ንቱም ጊዜ ቢሆን በሚመጡትም ጊዜያት
ᏽበመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይገለጥላቸዋል፣
ስለዚህ፣ የጌታ ᏽመንገድ አንድ ዘለዓለማዊ
ዙሪያ ነው።

፳ ስለዚህ የሰው ልጅ ሆይ፣ አስታውስ፣
ለሥራህ ሁሉ ᏽወደፍርድ ትቀርባለህና።

፳፩ ስለዚህ ᏽበሙከራ ዘመንህ መጥፎ ነገ
ሮችን ማድረግ ከፈለግህ በእግዚአብሔር
የፍርድ ወንበር ፊት ᏽሳትፀዳ ትገኛለህ፣
እናም ምንም እርኩስ ነገር ከእግዚአብሔር
ጋር ሊኖር አይቻለውም፣ ስለዚህ ለዘለዓ
ለም ትጣላለህ።

፳፪ እናም መንፈስ ቅዱስ እነዚህን ነገሮች
እናገርና እንዳልደብቃቸው ዘንድ ስልጣን
ሰጥቶኛል።

ምዕራፍ ፲፩

*ኔፊ የጌታን መንፈስ አየ እና የህይወት ዛፍ
በራዕይ ታየው—እርሱም የእግዚአብሔ
ርን ልጅ እናት አየ እናም ስለእግዚአብ
ሔር ትህትና ተማረ—እርሱም የእግዚአ
ብሔርን በግ ጥምቀት አገልግሎትና ስቅ
ለት አየ—እናም ደግሞ የአስራ ሁለቱን
የበጉን ሐዋርያት ጥሪና አገልግሎት አየ።
ከ፯፲–፰፲፯፲ ም.ዓ. ገደማ።*

፩ እናም እንዲህ ሆነ አባቴ ያየውን ነገ
ሮች ለማወቅ ከፈለግሁ በኋላ፣ እናም ጌታ
ሊያሳውቀኝ እንደሚችል በማመን በልቤ
ᏽእያሰላሰልኩ ተቀምጬ ሳለሁ በጌታ መን
ፈስ፣ አዎን፣ በፊት አይቼው ወደማላውቀ
ውና ከዚህ በፊት በእግሮቼ ቆሜበት ወደ
ማላውቀው እጅግ ከፍ ያለ ᏽተራራ ᏽተወ
ሰድኩ።

፪ እነሆ መንፈስ፣ ምን ትፈልጋለህ?
አለኝ።

፫ እና እኔም አልሁ፥ አባቴ ᏽያያቸውን ነገ
ሮች ማየት እፈልጋለሁ።

፬ እና መንፈስም አለኝ—አባትህ የተናገ
ረውን ᏽዛፍ እንዳየ ታምናለህን?

፭ እናም እኔ አልኩ—አዎን፣ የአባቴን
ቃላት በሙሉ ᏽእንደማምን አንተ ታው
ቃለህ።

፮ እናም እነዚህን ቃላት ስናገር መን
ፈስ በታላቅ ድምፅ እንዲህ ሲል ጮኸ፥
ሆሳዕና ለጌታ ለልዑል እግዚአብሔር፤
እርሱ ᏽበምድር ሁሉ ላይ፣ አዎን፣ ከሁ
ሉም በላይ አምላክ ነው። እናም አንተ፣
ኔፊ፣ የተባረክህ ነህ፣ ምክንያቱም አንተ
በልዑል እግዚአብሔር ልጅ ᏽአምነህልና፣
ስለዚህ የተመኘህቸውን ነገሮች ታያለህ።

፲፯መ ሞሮኒ ፲ ፡ ፬–፭ ፣ ፯ ፣ ፲፱።
ሠ ት. እና ቃ. ፳ ፡ ፳፯።
ረ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
፲፰ሀ ዕብ. ፲፫ ፡ ፰ ፣
ሞር. ፱ ፡ ፱ ፣
ት. እና ቃ. ፳ ፡ ፲፪።
ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣
አምላክ።
፲፱ሀ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር
ሚስጥሮች።
ለ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
ሐ አልማ ፯ ፡ ፳ ፣
ት. እና ቃ. ፫ ፡ ፪ ፣ ፴፭ ፡ ፩።
፳ሀ መክ. ፲፪ ፡ ፲፩ ፣
፪ ኔፊ ፱ ፡ ፵፯።
ቅ.መ.መ. ፍርድ፣
የመጨረሻው።
፳፩ሀ አልማ ፴፬ ፡ ፴፪–፴፭።
ለ ፩ ቆሮ. ፮ ፡ ፱–፣
፫ ኔፊ ፳፯ ፡ ፣፱ ፣
ት. እና ቃ. ፫፯ ፡ ፱–፰፪ ፣
ሙሴ ፮ ፡ ፶፯።
፲፩ ፩ሀ ት. እና ቃ. ፫፯ ፡ ፣፱።
ቅ.መ.መ. ማስላሰል።
ለ ዘዳግ. ፣ ፡ ፩ ፣
ኤተር ፫ ፡ ፩።
ሐ ፪ ቆሮ. ፣፪ ፡ ፩–፬ ፣
ራዕ. ፳፩ ፡ ፣ ፣
፪ ኔፊ ፬ ፡ ፳፭ ፣
ሙሴ ፩ ፡ ፩።
፫ ሀ ፩ ኔፊ ፳ ፡ ፪–፴፬።
፬ ሀ ፩ ኔፊ ፳ ፡ ፣–፣፪ ፣
፣፭ ፡ ፳፩–፳፪።
፭ ሀ ፩ ኔፊ ፪ ፡ ፣፯።
፮ ሀ ዘፀአ. ፱ ፡ ፳፱ ፣
፪ ኔፊ ፳፱ ፡ ፮ ፣
፫ ኔፊ ፣፩ ፡ ፣፬ ፣
ሙሴ ፮ ፡ ፴፬።
ለ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።

፯ እና እነሆ እነዚህ ነገሮች ለአንተ ᵐለም ልክት ይሰጡሀል፣ አባትህ የቀመሰውን ፍሬ የሚሰጠውን ዛፍ ካየህ በኋላ ደግሞም አንድ ሰው ከሰማይ ሲወርድ ታያለህ፣ እናም አንተ እርሱን ታያለህ፤ እናም ካየኸውም በኋላ የእ ግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ᵃትመሰክራለህ።

፰ እናም እንዲህ ሆነ መንፈስ እንዲህ አለኝ—ተመልከት! ተመለከትኩና ᵐዛፍን አየሁ፤ አባቴም እንዳየው አይነት ዛፍ ነበር፤ ውበቱም አዎን ከሁሉም ውብ ነገር የላቀ ነበር፤ ንጣቱም ከሚገፋው በረዶ ᵃንጣት የላቀ ነበር።

፱ እናም እንዲህ ሆነ ዛፉን ካየሁ በኋላ፣ ለመንፈሱ፥ ከሁሉ በላይ ᵐየከበረውን ዛፍ እንዳሳየኸኝ ተመለከትኩ አልኩት።

፲ እናም እርሱ፥ አንተ ምን ትፈልጋለህ? አለኝ።

፲፩ እናም እኔ ለእርሱ፥ ᵐትርጓሜውን ለማወቅ ነው አልኩት—እኔም ሰው እን ደሚናገረው ለእርሱ ተናገርኩት፤ ምክ ንያቱም እርሱ በሰው ᵃአምሳል እንደነበር ስለተመለከትኩ ነው፤ ይሁን እንጂ፣ የጌታ መንፈስ መሆኑን አውቅ ነበር፣ እናም ሰው ከሌላ እንደሚነጋገር እርሱ እኔን ተናገረኝ።

፲፪ እናም እንዲህ ሆነ እርሱ እኔን፥ ተመ ልከት! አለኝ፣ እኔም እርሱን ለመመልከት ዞርኩ እናም አላየሁትም ከእኔ ዘንድ ሄዶ ነበርና።

፲፫ እናም እንዲህ ሆነ እኔ ተመለከትኩ፣ እናም ታላቂቷን የኢየሩሳሌም ከተማ፣ ደግሞም ሌሎች ከተሞችን አየሁ። የናዝሬ ትንም ከተማ ተመለከትኩ፣ ᵐበናዝሬትም ከተማ አንዲት ᵃድንግል ተመለከትኩ፣ እርሷም እጅግ ውብና ያማረች ነበረች።

፲፬ እናም እንዲህ ሆነ ᵐሰማያት ሲከፈቱ አየሁ፤ እናም አንድ መልአክ ወረደና በፊቴ ቆመ፤ እንዲህም አለኝ፥ ኔፊ፣ ምን ትመ ለከታለህ?

፲፭ እናም አንዲት ከድንግሎች ሁሉ በላይ መልካም፣ በጣም ቆንጆ ድንግል፣ በማለት ተናገርኩት።

፲፮ እናም የእግዚአብሔርን ትህትና ታው ቃለህ? አለኝ።

፲፯ እናም እርሱ ልጆቹን እንደሚወድ አውቃለሁ፣ ይሁን እንጂ፣ የሁሉን ነገሮች ትርጉም አላውቅም አልኩት።

፲፰ እነሆ የተመለከትካት ᵐድንግል በስጋ የእግዚአብሔር ልጅ ᵃእናት ናት አለኝ።

፲፱ እናም እንዲህ ሆነ፣ እርሷ በመንፈስ እንደተወሰደች ተመለከትኩ፤ እና ለጥቂት ጊዜ ᵐበመንፈስ ከተወሰደች በኋላ መልአኩ እንዲህ ሲል ተናገረኝ፥ ተመልከት!

፳ እናም በድጋሚ ድንግሊቷ፣ በክንዷ ᵐልጅ ይዛ አየሁ፣ እንዲሁም ተመለከትኩ።

፳፩ እናም መልአኩ እንዲህ አለኝ፥ እነሆ ᵐየእግዚአብሔር በግ፣ አዎን እንዲያውም የዘላለማዊው ᵃአባት ᵐልጅ! አባትህ ያየውን ᵐዛፍ ትርጉም ታውቃለህ?

፳፪ እናም እንዲህ ስል መለስኩለት፤ አዎን፣ ይህ በሰው ልጆች ልብ ውስጥ ሁሉ ራሱን በስፋት የሚያፈስ የእግዚአብሔር ᵐፍቅር ነው፤ ስለዚህ ከሁሉ ነገሮች በላይ መልካም ነው።

፳፫ እርሱም፣ አዎን፣ ለነፍስም በጣም ᵐደስ የሚያሰኝ ነው አለኝ።

፳፬ እነዚህንም ነገሮች ካለ በኋላ፣ እንዲህ አለኝ—ተመልከት! እናም የእግዚአብሔር ልጅ በሰው ልጆች መካከል ᵐሲሄድ ተመ

፯ ᵐ ቅ.መ.መ. ምልክት።
ᵃ ቅ.መ.መ. ምስክርነት።
፰ ᵐ ፩ ኔፊ ፰፡ ፲።
ᵃ ፩ ኔፊ ፰፡ ፲፩።
፱ ᵐ ፩ ኔፊ ፲፩፡ ፳፪–፳፭።
፲፩ ᵐ ዘፍጥ. ፴፡ ፰።
ᵃ ኤተር ፫፡ ፲፭–፲፯።
፲፫ ᵐ ማቴ. ፪፡ ፳፫።
ᵃ ሉቃ. ፩፡ ፳፯–፳፯፣ አልማ ፯፡ ፲።
ᵐ ቅ.መ.መ. ማርያም፣ የኢየሱስ እናት።
፲፬ ᵐ ሕዝ. ፩፡ ፩፣ ፩ ኔፊ ፩፡ ፰።
፲፭ ᵐ ኢሳ. ፶፡ ፲፬፣ ሉቃ. ፩፡ ፴፬–፴፭።
ᵃ ሞዛያ ፫፡ ፰።
፲፱ ᵐ ማቴ. ፩፡ ፳።
ᵃ ሉቃ. ፪፡ ፲፯።
፳፩ ᵐ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር በግ።
ᵃ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ—እግዚአብሔር አብ።
ᵃ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ።
ᵐ ፩ ኔፊ ፰፡ ፲፣ አልማ ፭፡ ፰፪።
ᵐ ቅ.መ.መ. የህይወት ዛፍ።
፳፪ ᵐ ቅ.መ.መ. ፍቅር።
፳፫ ᵐ ቅ.መ.መ. ደስታ።
፳፬ ᵐ ሉቃ. ፪፡ ፲፬–፳፭።

ለከትኩ፤ ብዙዎችም በእግሩ ስር ሲወድቁና ሲሰግዱለት ተመለከትኩ።

፳፩ እናም እንዲህ ሆነ አባቴ ያየው [ሀ]የብረት በትር፣ ወደ [ለ]ህይወት ውሃዎች ምንጭ፣ ወይንም ወደ [ሐ]ህይወት ዛፍ፣ የሚመራው የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ ተመለከትኩ፤ ውሃዎቹም የእግዚአብሔር ፍቅር ምልክት ናቸው፤ ደግሞም የህይወት ዛፉም የእግዚአብሔር ፍቅር ምልክት መሆኑን አየሁ።

፳፪ እናም መልአኩ እንደገና እንዲህ አለኝ—የእግዚአብሔርን [ሀ]ትህትና እይ እንዲሁም ተመልከት አለኝ።

፳፫ እናም እኔ [ሀ]ተመለከትኩና አባቴ የተናገረለትንም የዓለም መድኃኒት ተመለከትኩ፣ ደግሞም ከእርሱ በፊት መንገዱን የሚያዘጋጀውን [ለ]ነቢይ ተመለከትኩ። የእግዚአብሔርም በግ ሄዶ በእርሱ [ሐ]ተጠመቀ፣ ከተጠመቀም በኋላ፣ ሰማያት ሲከፈቱና መንፈስ ቅዱስ ከሰማይ ሲወርድና [መ]በእርግብ አምሳል በእርሱ ላይ ሲያርፍ ተመለከትኩ።

፳፬ እናም እርሱ ህዝቡን [ሀ]በኃይልና በታላቅ ክብር እያገለገለ ሲሄድ ተመለከትኩ፤ ብዙ ህዝብም ሊያዳምጡት ተሰበሰቡ፤ ከመካከላቸው ሲያስወጡትም ተመለከትኩ።

፳፭ እናም ደግሞ ሌሎች [ሀ]አስራ ሁለት ሲከተሉት ተመለከትኩ። እናም እንዲህ ሆነ ከፊቴ በመንፈስ ተወሰዱም ተሰወሩ ብኝም።

፳፮ እናም እንዲህ ሆነ መልአኩ በድጋሚ እንዲህ አለኝ፣ ተመልከት! እናም ተመለከትኩና፣ ሰማያት እንደገና ሲከፈቱ ተመለከትኩ፣ [ሀ]መላዕክትም በሰው ልጆች ላይ ሲወርዱ አየሁ፤ እነርሱንም አገለገሏቸው።

፳፯ እንደገናም እንዲህ ሲል ተናገረኝ፥ ተመልከት! እኔም ተመለከትኩ፣ እናም የእግዚአብሔር በግ በሰው ልጆች መካከል ሲሄድ ተመለከትኩ። ብዛት ያላቸው የታመሙ እና በብዙ በሽታዎች፣ [ሀ]በአጋንንትና [ለ]በርኩሳን መናፍስት የሚሰቃዩ ሰዎችንም ተመለከትኩ፣ መልአኩም እነዚህን ሁሉ ነገሮች ለእኔ ተናገረም አሳየኝም። እነርሱም በእግዚአብሔር በግ ኃይል [ሐ]ተፈወሱ፣ እናም አጋንንትና ርኩሳን መናፍስትም ወጥተዋል።

፳፰ እናም እንዲህ ሆነ መልአኩ በድጋሚ እንዲህ ሲል ተናገረ—ተመልከት! እኔም የእግዚአብሔር በግ በሰዎች ሲወሰድ ተመለከትኩ፣ አዎን፣ የዘለዓለማዊው እግዚአብሔር ልጅ በዓለም [ሀ]ተፈረደበት፤ እኔም አየሁ፣ ምስክርም ሰጠሁ።

፳፱ እናም እኔ ኔፊ፣ ለዓለም ኃጢያት [ሀ]በመስቀል ላይ ሲሰቀልና [ለ]ሲገደል ተመለከትኩ።

፴ እናም እርሱ ከተገደለ በኋላ የምድሪቱ ሰዎች የበጉን ሐዋርያት ለመዋጋት ሲሰበሰቡ ተመለከትኩ፣ ምክንያቱም እንደዚህ ነበር አስራ ሁለቱ በጌታ መልአክ የተጠሩት።

፴፩ እናም ብዙ የምድሪቱ ሰዎች በአንድነት ተሰበሰቡ፤ አባቴም እንዳየው ህንፃ አይነት ትልቅና ሰፊ [ሀ]ህንፃ ውስጥ እንደ ነበሩ ተመለከትኩ። እናም የጌታ መልአክ እንዲህ ሲል እንደገና ተናገረኝ፥ እነሆ ዓለ

፳፩ ሀ ፩ ኔፊ ፰፡፲፱።
ለ ቅ.መ.መ. ህያው ውሀ።
ሐ ዘፍጥ. ፪፡፱፣
አልማ ፴፪፡፣ ፴–፴፭፣
ሙሴ ፮፡ ፳፰፡ ፴፭።
፳፪ ሀ ፩ ኔፊ ፲፭፡፲፯–፴፫።
፳፫ ሀ ፪ ኔፊ ፳፭፡፲፫–፴፣
ለ ማቴ. ፲፭፡ ፲፣
፩ ኔፊ ፲፡ ፯–፲፣
፪ ኔፊ ፴፭፡ ፀ።
ሐ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣
መጥመቅ።
መ ቅ.መ.መ. የርግብ
መልእክት።
፳፰ ሀ ት. እና ቃ. ፻፴፰፡ ፳፭–፳፯።
፳፱ ሀ ቅ.መ.መ. ሐዋሪያ።
፴ ሀ ቅ.መ.መ. መላእክት።
፴፩ ሀ ማር. ፭፡ ፲፭–፳፣
ሞዛያ ፫፡ ፭–፯።
ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
ለ ቅ.መ.መ. መንፈስ—ክፉ
መንፈሶች።
ሐ ቅ.መ.መ. መፈወስ፣
ፈውሶች።
፴፪ ሀ ማር. ፲፭፡ ፲፯–፳።
፴፫ ሀ ዮሐ. ፲፱፡ ፲፯–፲፱፣
ሞዛያ ፫፡ ፱–፲፣
፫ ኔፊ ፳፯፡ ፲፡።
ቅ.መ.መ. መስቀል።
ለ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ዋጋን
መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ።
፴፭ ሀ ፩ ኔፊ ፲፡ ፳፯፣ ፲፪፡ ፲፲፡።

ምና በውስጧ ያለው ጥበብ፣ አዎን፣ እነሆ የእስራኤል ቤት የበጉን አስራ ሁለት ሐዋር ያት ለመዋጋት በአንድነት ተሰበሰቡ።

፴፮ እናም እንዲህ ሆነ ትልቁና ሰፊው ህንፃ የዓለም ᵐኩራት መሆኑን አየሁ፣ መሰከርኩም፤ ይህም ወደቀ፣ ውድቀቱም እጅግ ታላቅ ነበር። በድጋሚም የጌታ መል አክ እንዲህ ሲል ተናገረኝ፥ አስራ ሁለቱን የበጉን ሐዋርያት የሚዋጉ ሀገሮች፣ ነገ ዶች፣ ቋንቋዎችና ህዝቦች ሁሉ ውድቀት እንዲህ ይሆናል።

ምዕራፍ ፲፱

ኔፊ የቃልኪዳኑን ምድር፣ የነዋሪዎችዋን ጻድቅነት፣ ኃጢያት እና ጥፋትን፤ የእግ ዚአብሔርን በግ በእነርሱ መካከል መም ጣትን፤ አስራ ሁለቱ ደቀመዛሙርት እና አስራ ሁለቱ ሐዋርያት እስራኤልን እን ዴት እንደሚፈርዱ፣ እና በእምነት ማጣት የመነመኑትን አሰቃቂና መጥፎ ሁኔታ በራ ዕይ አየ። ከ፲፯–፳፯፲፭ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ መልአኩ እንዲህ አለኝ፥ ተመልከት፣ እነሆ ያንተን ዘሮች፣ ደግሞም የወንድሞችህን ዘሮች እይ። እኔም ተመለከትኩና ᵐየቃል ኪዳንን ምድር አየሁ፤ አዎን፣ ቁጥራቸው እንደባህር አሸዋ እንደሆነ ያህል ብዛት ያላቸውን ህዝቦች ተመለከትኩ።

፪ እናም እንዲህ ሆነ ብዛት ያላቸው ህዝ ቦች እርስ በእርስ ለመዋጋት በአንድነት ተሰባስበው አየሁ፤ እናም በህዝቦቼ መካ ከል ᵐጦርንና የጦር ወሬን፣ እና በጎራዴ ታላቅ የሆኑ ግድያዎችን አየሁ።

፫ እናም እንዲህ ሆነ በፀብና በጦርነት ሁኔታ ውስጥ በምድሪቱ ብዙ ትውልድ ሲያልፍ አየሁ፤ እናም፣ አዎን፣ ብዙ ያል ቆጠርኳቸውን ከተማዎችን እንኳን ተመ ለከትኩ።

፬ እናም እንዲህ ሆነ በቃልኪዳኑ ምድር ላይ ᵐየጨለማ ᵃጭጋግን ተመለከትኩ፤ መብረቅንም አየሁ፣ የነጎድጓድንም ድምፅ፣ የመሬት መንቀጥቀጥና የተለያዩ አሰቃቂ የሆኑ ድምፆችን ሁሉ ሰማሁ፤ ምድርና አለቶች ሲሰነጠቁም አየሁ፤ ተራሮች እየ ተሸረፉ ሲንከባለሉም አየሁ፣ ለጥ ያሉ የም ድር ሜዳዎች ሲሰባበሩም አየሁ፤ ᵐየሰመጡ ብዙ ከተሞችም አየሁ፣ በእሳት የተቃጠሉ ብዙዎችንም አየሁ፤ በመሬት መንቀጥቀጥ ምክንያት የፈረሱ ብዙዎችንም አየሁ።

፭ እናም እንዲህ ሆነ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ካየሁ በኋላ፣ ᵐየጨለማ ጭጋግ ከምድር ገፅ ሲጠፋ አየሁ፣ እናም እነሆ በጌታ ታላቅና አስፈሪ ፍርድ ምክንያት ያልጠፉ ብዙዎ ችን ተመለከትኩ።

፮ እናም ሰማያት ሲከፈቱና ᵐየእግዚአብ ሔር በግ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ፣ እርሱም ወረደና እራሱን አሳያቸው።

፯ እናም መንፈስ ቅዱስ በሌሎች ᵐአስራ ሁለት ላይ እንደወረደም ተመለከትኩም፣ እመሰክራለሁም፤ እነርሱም በእግዚአብ ሔር የተሾሙና የተመረጡ ነበሩ።

፰ እናም መልአኩ እንዲህ ሲል ተናገ ረኝ—እነሆ የአንተን ዘር እንዲያገለግሉ የተመረጡትን አስራ ሁለቱን የበጉን ደቀ መዛሙርት ተመልከት።

፱ እናም እርሱ እንዲህ አለኝ—የበጉን ᵐአስራ ሁለት ሐዋሪያት ታስታውሳለህን? እነሆ የእስራኤል አስራ ሁለቱን ነገዶች ᵃየሚፈርዱት እነርሱ ናቸው፤ ስለዚህ እና ንተ ከእስራኤል ቤት ናችሁና አስራ ሁለቱ የዘርህ አገልጋዮች በእነርሱ ይፈረዳሉ።

፲ እናም ያየሀቸው እነዚህ ᵐአስራ ሁለቱ

፴፮ *ሀ* ቅ.መ.መ. ኩራት።
፲፱ ፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. የቃል ኪዳን ምድር።
፪ *ሀ* ኢኖስ ፩፡ ፳፬፡ ሞር. ፰፡ ፯–፰። ቅ.መ.መ. ጦርነት።
፬ *ሀ* ፩ ኔፊ ፲፱፡ ፲።
ለ ሔለ. ፲፩፡ ፳–፳፰።
ሐ ፫ ኔፊ ፰፡ ፲፩።
፭ *ሀ* ፫ ኔፊ ፰፡ ፳፣ ፲፡ ፱።
፮ *ሀ* ፪ ኔፊ ፳፮፡ ፩፣ ፱፣ ፫ ኔፊ ፲፩፡ ፲፯–፲፯።
፯ *ሀ* ፫ ኔፊ ፲፪፡ ፩፣ ፲፱፡ ፲፪–፲፫።
፱ *ሀ* ፡ ኦቃ. ፯፡ ፲፫።
ለ ማቴ. ፲፱፡ ፳፰፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡ ፲፪። ቅ.መ.መ. ፍርድ፣ የመጨረሻው።
፲ *ሀ* ፫ ኔፊ ፳፯፡ ፳፯፣ ሞር. ፫፡ ፲፰–፲፱።

አገልጋዮች በዘርህ ላይ ይፈርዳሉ። እናም እነሆ ለዘለዓለም ፃድቃን ናቸው፤ በእግዚአብሔር በግ ባላቸው እምነት ምክንያት ፡ልብሳቸው በደሙ ነፅቶአልና።

፲፩ መልአኩም አለኝ—ተመልከት! እኔም ተመለከትኩ፣ እናም እነሆ ፡ሶስት ትውልዶች በፅድቅ ሲያልፉ ተመለከትኩ፤ ልብሳቸውም እንደ እግዚአብሔር በግ ነጭ ነበር። መልአኩም አለኝ—እነዚህ በእርሱ ባላቸው እምነት ምክንያት በበጉ ደም ነፅተዋል።

፲፪ እናም እኔ ኔፊ ደግሞ በፅድቅ ያለፉትን ፡የአራት ትውልዶች ብዙዎችን ተመለከትኩ።

፲፫ እናም እንዲህ ሆነ የምድር ብዙዎች በአንድ ላይ ተሰብስበው አየሁ።

፲፬ መልአኩም እንዲህ አለኝ—ዘርህን፣ እንዲሁም ደግሞ የወንድሞችህን ዘሮች ተመልከት።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ እነሆ የእኔ ዘር የሆኑትን በብዛት በወንድሞቼ ዘር ፡ላይ በአንድ ላይ ተሰብስበው ተመለከትኩ፣ እናም እነርሱ በአንድ ላይ ለመዋጋት ተሰብስበው ነበር።

፲፮ መልአኩምም እንዲህ ብሎ ተናገረኝ—እነሆ አባትህ ያየው ፡መጥፎ ውሃ ምንጭ፣ አዎን፣ የተናገረው ፡ወንዙ፤ የእዚህም ጥልቀት እንደ ፡ሲኦል ጥልቅ ነው።

፲፯ ፡ዐይኖችንም የሚያሳውሩና የሰውልጆችን ልብ የሚያጠጥሩ፣ እና እንዲሰቱና እንዲጠፉ ወደ ፡ሰፊው ጎዳና እነርሱን የሚመሩ ፡የጨለማው ጭጋጋት የዲያብሎስ ፈተናዎች ናቸው።

፲፰ እናም አባትህ ያየው ትልቁና ሰፊው ፡ህንፃ የሰው ልጆች ከንቱ ፡ሀሳብና ፡ኩራት ነው። እናም ትልቅ አስፈሪ ፡ገደል፣ አዎን፣ እንዲሁም የዘለዓለማዊው አምላክ ፡ፍትህ ቃል፣ መንፈስ ቅዱስ ከዓለም መጀመሪያ ጀምሮ እስከ አሁንና፣ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ለዘለአለም የሚመሰክርለት፣ የእግዚአብሔር በግ የሆነው መሲህ ይለያቸዋል።

፲፱ መልአኩም እነዚህን ቃላት ሲናገር፣ መልአኩ ይሆናሉ ብሎ እንደተናገረው የወንድሞቼ ዘር ከእኔ ዘር ጋር ሲቃረን አየሁ፤ በእኔ ዘር ኩራትና በዲያብሎስ ፡ፈተናዎች ምክንያት የወንድሞቼ ዘር የእኔን ዘር ህዝቦች ፡ሲያሸንፉ አየሁ።

፳ እናም እንዲህ ሆነ የእኔን ዘር ያሸነፉትን የወንድሞቼን ዘር ህዝቦች ተመለከትኩ፣ አየሁም፤ እነርሱም በምድር ላይ በብዛት ሆነው ሄዱ።

፳፩ እናም እነርሱ በብዛት በአንድ ላይ ተሰብስበው ተመለከትኩ፤ በእነርሱም መካከል ፡ጦርነትና የጦርነት ወሬዎችን ተመለከትኩ፤ በጦርነትና በጦርነት ወሬዎችም ብዙ ትውልዶች ሲያልፉ ተመለከትኩ።

፳፪ እናም መልአኩ እንዲህ አለኝ—እነርሱ እምነት በማጣት ፡ይመነምናሉ።

፳፫ እናም እንዲህ ሆነ እነሆ እነርሱ እምነት በማጣት ከመነመኑ በኋላ ፡ስራዕትና በሁሉም አይነት ርኩሰቶች የተሞሉ፣ ፡የጠቆሩና፣ ፡አፀያፊና መጥፎ ሰዎች ሆኑ።

ምዕራፍ ፲፫

ኔፊ በአህዛቦች መካከል የዲያብሎስ ቤተ

፲ ለ ራዕ. ፯፡ ፲፱፤
አልማ ፭፡ ፳፩–፳፯፤
፲፫፡ ፲፩–፲፫፤
፫ ኔፊ ፳፯፡ ፲፱–፳፡
፲፩ ሀ ፪ ኔፊ ፳፯፡ ፱–፲፡
፫ ኔፊ ፳፯፡ ፴–፴፪፡
፲፪ ሀ አልማ ፴፭፡ ፲–፲፪፤
ሔለ. ፲፫፡ ፭፣ ፱–፲፡
፫ ኔፊ ፳፯፡ ፴፪፤
፴ ኔፊ ፩፡ ፲፡–፳፯።
፲፭ ሀ ሞር. ፯።
፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. እድፍ፣
እድፍነት።
ለ ፪ ኔፊ ፳፡ ፲፫፤ ፲፭፡ ፳፯–፳፱።
ሐ ቅ.መ.መ. ሲያል።
፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. ክህደት።
ለ ማቴ. ፯፡ ፲፫–፲፡።
ሐ ፪ ኔፊ ፳፡ ፳፫፤ ፲፭፡ ፳፡፤
ት. እና ቃ. ፲፡ ፳–፴፪።
፲፰ ሀ ፪ ኔፊ ፳፡ ፳፯፤
፲፩፡ ፴፭–፴፯።
ለ ኤር. ፯፡ ፳፡።
ሐ ቅ.መ.መ. ኩራት።
መ ሉቃ. ፲፯፡ ፳፯፤
፪ ኔፊ ፲፭፡ ፳፰–፴።
ሠ ቅ.መ.መ. ፍትህ።
፲፱ ሀ ቅ.መ.መ. መፈተን፣ ፈተና።
ለ ጄረም ፩፡ ፲፣
ቃላት ፩፡ ፩–፪።
፳፩ ሀ ሞር. ፳፡ ፳፣
ሞሮኒ ፩፡ ፪።
ቅ.መ.መ. ጦርነት።
፳፪ ሀ ፩ ኔፊ ፲፫፡ ፲፫፣
፪ ኔፊ ፳፯፡ ፲፫።
፳፫ ሀ ቅ.መ.መ. ስራ ሰልቺ፣ ስራ
ፈቺ።
ለ ፪ ኔፊ ፳፯፡ ፴፫።
ሐ ፪ ኔፊ ፭፡ ፳–፳፭።

ክርስቲያን መቋቋምን፣ የአሜሪካ መገኘ ትና ቅኝ መያዝን፣ የመፅሐፍ ቅዱስ ብዙ የተከበሩና ግልፅ ክፍሎች መጥፋትን፣ የእዚህም ውጤት የሆነውን የአሕዛብ ክህ ደት ሁኔታን፣ የወንጌል መመለስን፣ የኋ ለኛው ቀን ቅዱስ መፅሐፍት መምጣትን፣ እና የፅዮንን ግንባታ በራዕይ አየ። ከ፲፪–፲፭ ፲፣ ፲፯ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ መልአኩ እንዲህ ሲል ተናገረኝ—ተመልከት! እናም እኔ ብዙ ሀገሮችንና መንግስታትን ተመለከትኩ።

፪ መልአኩም ምን አየህ? አለኝ፣ እናም ብዙ ሀገሮችና መንግስታትን ተመለከትኩ አልኩት።

፫ እናም እርሱ እነዚህ የአህዛብ ሀገሮችና መንግስታት ናቸው አለኝ።

፬ እናም እንዲህ ሆነ [1]በአሕዛብ ሀገሮች መካከል [2]ትልቅ ቤተክርስቲያን ሲቋቋም አየሁ።

፭ መልአኩም አለኝ፣ ከሌሎች ቤተክር ስቲያኖች ሁሉ በላይ የርኩሰቱን ቤተክርስ ቲያን አመሰራረት ተመልከት፣ ይኸውም የእግዚአብሔርን ቅዱሳን [3]የሚገድለውን፣ አዎን፣ ያሰራቸዋልም፣ ያሰቃያቸዋልም፣ በብረት [4]ቀንበርም ይጠምዳቸዋል፣ በኃይ ልም ይማርካቸዋል።

፮ እናም እንዲህ ሆነ ይህን [5]ታላቋና የርኩ ሰቱን ቤተክርስቲያን ተመለከትኩ፤ መስራ ቹም [6]ዲያብሎስ እንደሆነም አየሁ።

፯ ደግሞም [7]ወርቅ፣ ብር፣ ሐርና፣ ቀይ ግምጃዎች እናም የተፈተለ ጥሩ በፍታ፣ እንዲሁም ሁሉም አይነት የከበሩ ልብሶ ችን አየሁ፤ ብዙ ጋለሞታዎችንም አየሁ።

፰ መልአኩም እንዲህ ሲል ተናገረኝ—እነሆ ወርቁና፣ ብሩና፣ ሐሩና፣ ቀይ ግም ጃዎችና፣ የተፈተለ ጥሩ በፍታን፣ እንዲ ሁም የከበሩት ልብሶችና ጋለሞታዎች፣ የዚህ ታላቋና የርኩሰት ቤተክርስቲያን [8]ፍላጎቶች ናቸው።

፱ እናም ደግሞ ለዓለም ምስጋና ሲሉ የእግዚአብሔርን ቅዱሳን [9]ያጠፋሉ፣ ወደ ምርኮም ያመጧቸዋል።

፲ እናም እንዲህ ሆነ እነሆ ተመለከትኩና ብዙ ውኃዎችን አየሁ፤ እናም እነርሱም አህዛቦችን ከወንድሞቼ ዘር ያለያያሉ።

፲፩ እናም እንዲህ ሆነ መልአኩ አለኝ፣ እነሆ የእግዚአብሔር ቁጣ በወንድሞችህ ዘር ላይ ነው።

፲፪ እናም ከወንድሞቼ ዘር በብዙ ውሀዎች ተለይተው ከነበሩ አህዛብ መካከል አንድ ሰው አየሁና ተመለከትኩ፤ [10]የእግዚአብ ሔር መንፈስ ወርዶ በሰውየው ላይ ሲሰ ራም አየሁ፤ እናም የወንድሞቼ ዘር ወዳ ለበት ወደ ቃልኪዳኑ ምድር እንኳን በብዙ ውኃዎች ላይ ሄደ።

፲፫ እናም እንዲህ ሆነ የእግዚአብሔርን መንፈስ በሌሎች አህዛቦች ላይ እንደሰራ ተመለከትኩ፣ እናም እነርሱ ከምርኮ ወጥ ተው በብዙ ውኃዎች ላይ ተጓዙ።

፲፬ እናም እንዲህ ሆነ ከአህዛብ ብዙ [11]ሰዎችን [12]በቃልኪዳኑ ምድር ላይ ተመ ለከትኩ፤ የእግዚአብሔርም ቁጣ በወን ድሞቼ ዘር ላይ እንደነበረ ተመለከትኩ፣ እነርሱም በአህዛቦች ፊት [13]የተበተኑ፣ እና የተመቱም ነበሩ።

፲፭ እናም የጌታ መንፈስ በአህዛቦች ላይ እንደነበረ ተመለከትኩ፣ እነርሱም በለፀጉ፣ [14]ምድሪቱንም ለርስታቸው ያዙ፤ እነርሱም የነጡና ልክ [15]ከመገደላቸው በፊት እንደነ

---

[1] ፲፫ ፩ሀ ቅ.መ.መ. አህዛቦች።
ለ ፩ ኔፊ ፲፫፡፳፯፣ ፴፯፣ ፴፱፡ ፲፡ ፱–፲፯።
፩ ፩ሀ ራዕ. ፲፯፡ ፲–፣ ፱–፲፯።
፩ ፩ ኔፊ ፲፡ ፲፫።
ለ ኤር. ፳፯፡ ፲–፲፡።
፯ ፩ሀ ት. እና ቃ. ፹፯፡ ፶፡።
ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ—የዲያብሎስ ቤተክርስቲያን።
ለ ፩ ኔፊ ፳፪፡ ፳፪–፳፫፡።
፯ ፩ሀ ሞር. ፰፡ ፴፯–፴፰።
፰ ፩ሀ ራዕ. ፲፯፡ ፲–፣ ፴፩፣ ሞር. ፰፡ ፴፩–፴፰።
፱ ፩ሀ ራዕ. ፲፫፡ ፱–፡።
፲፪ ፩ሀ ቅ.መ.መ. መነሳሻ፣ መነሳሳት።
፲፡ ፩ሀ ፪ ኔፊ ፩፡ ፲፩፣ ሞር. ፭፡ ፲፱–፳።
ለ ቅ.መ.መ. የቃል ኪዳን ምድር።
ሐ ፩ ኔፊ ፳፪፡ ፯–፰።
ቅ.መ.መ. እስራኤል—የተበተኑት እስራኤል።
፲፭ ፩ሀ ፪ ኔፊ ፲፡ ፲፱።
ለ ሞር. ፮፡ ፲፯–፳፪።

በሩት እንደ ህዝቦቼ እጅግ [ሐ]ያማሩ እንደነ
በሩ ተመለከትኩ።
፲፮ እናም እንዲህ ሆነ እኔ ኔፊ ከምርኮ
ወጥተው የሄዱት አህዛቦች በጌታ ፊት እራ
ሳቸውን እንዳዋረዱ ተመለከትኩ፣ እናም
የጌታ ኃይልም [ሀ]ከእነርሱ ጋር ነበር።
፲፯ እናም የአህዛቦች እናት ሀሮች በውኃ
ዎቹ ላይ እንዲሁም ደግሞ በምድሩ ላይ
ከእነርሱ ጋር ለመዋጋት በአንድ ላይ ተሰ
ብስበው እንደነበር አየሁ።
፲፰ እናም የእግዚአብሔር ኃይል ከእነርሱ
ጋር እንደነበር፣ ደግሞም የእግዚአብሔር
ቁጣ እነርሱን ለመዋጋት በአንድ ላይ በተ
ሰበሰቡት ላይ ሁሉ እንደነበር ተመለከትኩ።
፲፱ እናም እኔ ኔፊ ከምርኮ የወጡት አህ
ዛብ ከሌሎች ሀገሮች እጆች በእግዚአብሔር
ኃይል [ሀ]የዳኑ እንደሆነ አየሁ።
፳ እናም እንዲህ ሆነ እኔ ኔፊ በምድሪቱ
እነርሱ በልፅገው አየሁ፣ እናም [ሀ]መጽሐ
ፍን አየሁ፤ በመካከላቸውም ይዘውት እየ
ሄዱም ነበር።
፳፩ እናም መልአኩ እንዲህ አለኝ—የመ
ፅሐፉን ትርጉም ታውቃለህን?
፳፪ እናም አላውቀውም አልኩት።
፳፫ እርሱም አለ—እነሆ ይህ ከአይሁድ
አፍ የወጣ ነው። እኔ ኔፊም ተመለከትኩ፤
እርሱም እንዲህ አለኝ—አንተ ያየኸው
[ሀ]መፅሐፍ [ለ]የአይሁዶች [ሐ]መዝገብ ነው፤
ይህም እርሱ ከእስራኤል ቤት ጋር ያደረገ
ውን የጌታን ቃልኪዳኖች የያዘ ነው፤ እናም
ደግሞ የቅዱሳን ነቢያትን ብዙ ትንቢቶች
የያዘ ነው፤ ይህም ብዙ ትንቢቶች ካለመ
ኖራቸው በስተቀር ልክ [መ]በነሀስ ሰሌዳዎች
ላይ እንደተቀረፁት አይነት መዝገብ ነው፤
ሆኖም ጌታ ለእስራኤል ቤት የገባውን ቃል
ኪዳኖች ይዘዋል፤ ስለዚህ እነርሱ ለአህዛብ
ታላቅ ዋጋ አላቸው።
፳፬ የጌታ መልአክም አለኝ—ከአይሁድ
አፍ የወጣውን መፅሐፍ ተመልክተሀል፤
እናም ከአይሁድ አፍ በወጣ ጊዜ አስራ
ሁለቱ ሐዋርያት የመሰከሩለትን የጌታን
ወንጌል ሙሉነት ይዟል፤ እነርሱም በእግ
ዚአብሔር በግ ውስጥ ባለው እውነታ መሰ
ረት መሰከሩ።
፳፭ ስለዚህ እነዚህ ነገሮች በእግዚአብ
ሔር ውስጥ ባለው እውነታ መሰረት [ሀ]ከአይ
ሁዶች ወደ [ለ]አህዛብ በንፅህና ይተላለፋሉ።
፳፮ እናም ከአይሁዶች [ሀ]ወደ አህዛብ በአ
ስራ ሁለቱ የበጉ ሐዋርያት እጆች ከተላ
ለፈ በኋላ ከሌሎች ሁሉ ቤተክርስቲያኖች
በላይ የበለጠ የረከሰውን [ለ]ታላቋና የርኩ
ሰቱን [ሐ]ቤተክርስቲያን መመስረት ተመ
ልክተሀል፤ እነሆም እነርሱ ከበጉ ወንጌል
[መ]ግልፅና እጅግ የከበሩትን ብዙ ክፍሎች
[ሠ]ወስደዋል፤ ደግሞም ብዙ የጌታን ቃል
ኪዳኖች አጥፍተዋል።
፳፯ እናም ይህን ሁሉ ነገር ያደረጉት
የጌታን መንገድ ያጣምሙ ዘንድ፣ የሰው
ልጆች ዐይናቸውን ያሳውሩና፣ ልባቸውን
ያጠጥሩ ዘንድ ነበር።
፳፰ ስለዚህ መፅሐፉ በታላቋና በርኩ
ሰቱ ቤተክርስቲያን እጆች ውስጥ ካለፉ
በኋላ የእግዚአብሔር በግ መፅሐፍ ከሆነው
መፅሐፍ ውስጥ ብዙ ግልፅና የከበሩ ነገሮች
መወሰዳቸውን ተመልክተሀል።
፳፱ እናም እነዚህ ግልፅና የከበሩ ነገሮች
ከተወሰዱ በኋላ ወደ አህዛቦች ሀገሮች ሁሉ
ተወሰዷል፤ ለሁሉም የአህዛብ ሀገሮች፣
አዎን፣ እንዲሁም በብዙ ውኃዎች አቋር
ጠው ሲሄዱ አንተ ካየሀቸው ከምርኮ ከወ

፲፭ሐ ፪ ኔፊ ፭፥፳፩።
፲፮ሀ ት. እና ቃ. ፻፩፥፹።
፲፱ሀ ፪ ኔፊ ፲፥፲–፲፬፤
፫ ኔፊ ፳፩፥፬፤
ኤተር ፪፥፲፪።
፳ሀ ፩ ኔፊ ፲፬፥፳፫።
፳፫ሀ ፩ ኔፊ ፲፫፥፴፰፤
፪ ኔፊ ፳፱፥፬–፲፪።
ለ ፪ ኔፊ ፫፥፲፪።
ሐ ቅ.መ.መ. ቅዱሳት
መጻህፍት።
መ ፩ ኔፊ ፭፥፲–፲፫።
፳፭ሀ ፪ ኔፊ ፳፱፥፬–፮፤
ት. እና ቃ. ፫፥፲፮።
ቅ.መ.መ. አይሁዶች።
ለ ቅ.መ.መ. አህዛቦች።
፳፮ሀ ማቴ. ፳፩፥፵፫።
ለ ፩ ኔፊ ፲፫፥፬–፮፤
፲፬፥፫፣ ፱–፲፯።
ሐ ቅ.መ.መ. ክህደት—
የመጀመሪያ የክርስትያን
ቤተክርስትያን ክህደት።
መ ፩ ኔፊ ፲፬፥፳–፳፮፤
እ.አ. ፩፥፰።
ሠ ሞር. ፰፥፴፫፤
ሙሴ ፩፥፵፩።

ጡት ከአህዛብ ጋር ከተወሰደ በኋላ—ይኸ ውም በእግዚአብሔር በግ ውስጥ በሆነው ግልፅነት መሰረት ለሰው ልጆች ግንዛቤ ግልፅ የነበሩት ብዙ ግልፅና የከበሩ ነገሮች ከመፅሐፉ በመወሰዳቸው ምክንያት—ከበጉ ወንጌል እነዚህ ነገሮች በመወሰዳቸው ምክ ንያት እጅግ ታላቅ ብዙዎችም፣ አዎን፣ ሰይጣንም እንኳን በእነርሱ ላይ ትልቅ ኃይል እስኪያገኝ ድረስ ተሰናከሉ።

፴ ሆኖም ከምርኮ የወጡትን አህዛብ ጌታ እግዚአብሔር ከአባትህ ጋር ዘሮቹ [ሀ]የርስት ምድር ይኖራቸው ዘንድ ቃል ኪዳን የገባ ለት ምድር በሆነው፣ ከሌሎች ምድር ሁሉ በላይ በመረጠው የምድር ገፅ ላይ በእግዚ አብሔር ሀይል ከሌሎች ሀገሮች ሁሉ በላይ ጠንካራ እንደተደረጉ ተመልክተሃል፤ ስለ ዚህ ጌታ እግዚአብሔር ከወንድሞችህ ዘሮች ጋር [ለ]የተቀላቀሉትን ያንተን ዘሮች አህዛብ ፈፅሞ እንዲያጠፏቸው አንደማይፈቅድም አይተሀል።

፴፩ አህዛብም የወንድሞችህን ዘር [ሐ]እንዲ ያጠፉ እርሱ አይፈቅድም።

፴፪ ጌታ እግዚአብሔር አህዛብ፣ ይኸውም የነበሩበትን እንደተመለከትከው፣ ግልፅና እጅግ የከበረው የበጉ ወንጌል ክፍል ሲሰራ ባየኸው [መ]በርኩሰቱ ቤተክርስቲያን ወደኋላ በመያዛቸው ምክንያት፣ በዚያ አስቃቂ በሆ ነው እውርነት ለዘለዓለም እንዲቀሩም አይ ፈቅድም።

፴፫ ስለዚህ የእግዚአብሔር በግ አለ—የእ ስራኤልን ቤት ቅሪት በታላቅ ፍርድ በመ ጎብኘት ለአህዛብ ምህረትን አደርጋለሁ።

፴፬ እናም እንዲህ ሆነ የጌታ መልአክ እን ዲህ ሲል ተናገረኝ—እነሆ የእግዚአብሔር በግ አለ፣ የእስራኤልን ቤት ቅሪት ከጎበኘ ኋቸው በኋላ፤ እናም እኔ የተናገርኩት ይህ [ሀ]ቅሪት የአባትህ ዘር ነው—ስለዚህ እነር ሱንም በፍርድ ከጎበኘኋቸው በኋላና በአ ህዛብም እጅ ከመታኋቸው በኋላ፣ እንዲ ሁም ይበልጥ ግልፅና የከበሩ [ለ]የበጉ ወን ጌል ክፍሎችን የጋለሞታዎች እናት በሆ ነችው የርኩሰት ቤተክርስቲያን በመወሰ ዳቸው ምክንያት አህዛብ እጅግ [ሐ]ከተሰና ከሉ በኋላ ይላል በጉ፤ በዚያን ቀን ለአህዛብ መሀሪ እሆናለሁ፣ በዚህም ለእነርሱ በእኔ ኃይል ግልፅና የከበረ የሚሆነውን ብዙውን ወንጌሌን ለእነርሱ [መ]አመጣለሁ ይላል በጉ።

፴፭ እነሆም በጉ አለ—እኔ ራሴን ለዘሮ ችህ እገልፃለሁ፣ እነርሱም የማስተምረውን ግልፅና የከበሩ ነገሮች ይፅፋሉ፣ የአንተም ዘሮች ከጠፉና እምነት በማጣት ከመነመኑ በኋላ፣ ደግሞም የወንድሞችህ ዘሮች እም ነት በማጣት ከመነመኑ በኋላ፣ እነሆ [ሠ]እነ ዚህ ነገሮች ለአህዛብ በበጉ ስጦታና ኃይል ይገለጡ ዘንድ ይደበቃሉ።

፴፮ እናም በጉ በእነዚህ ነገሮች ውስጥ የእኔ [ረ]ወንጌልና፣ [ሰ]አለትና ደህንነት ይጻፋሉ አለ።

፴፯ በእዚያም ቀን የእኔን [ሸ]ፅዮን ለማም ጣት የፈለጉት [ቀ]የተባረኩ ናቸው፣ እነርሱም የመንፈስ ቅዱስ ኃይልና [በ]ስጦታ ይኖራቸ ዋልና፤ እንዲሁም እስከ መጨረሻ [ተ]የሚ ፀኑ ከሆነ በመጨረሻው ቀን ከፍ ይደረ ጋሉ፣ በዘለአለማዊው የበጉ [ኘ]መንግስት ውስጥ ይድናሉም፤ እናም ሰላምን [ኀ]የሚ ያወሩ፣ አዎን የመልካምንም ወሬ የምስ

፴ ሀ ቅ.መ.መ. የቃል ኪዳን ምድር።
ለ አልማ ፴፭ ፡ ፲–፲፡፡
፴፩ ሀ ፪ ኔፊ ፡ ፯ ፤ ፲ ፡ ፲፰–፲፱ ፤ ያዕቆ. ፲ ፡ ፭–፱ ፤ ሔሌ. ፲፫ ፡ ፲፪ ፤ ፲ ኔፊ ፲፯ ፡ ፰–፱ ፤ ሞር. ፭ ፡ ፳–፳፩ ።
፴፪ ሀ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ—የዲያብሎስ ቤተክርስቲያን ።
፴፫ ሀ ቅ.መ.መ. ዮሴፍ፣ የያዕቆብ ልጅ ።
ለ ቅ.መ.መ. ወንጌል ።
ሐ ፩ ኔፊ ፲፡ ፡ ፩–፲ ፤ ፪ ኔፊ ፳፯ ፡ ፳ ።
መ ት. እና ቃ. ፲ ፡ ፳፪ ። ቅ.መ.መ. የወንጌል ዳግም መመለስ ።
፴፭ ሀ ፪ ኔፊ ፳፯ ፡ ፯ ፤ ፳፱ ፡ ፩–፪ ። ቅ.መ.መ. መፅሐፈ ሞርሞን ።
፴፯ ሀ ፲ ኔፊ ፳፯ ፡ ፲፫–፳፩ ።
ለ ሔሌ. ፭ ፡ ፲፪ ፤ ፲ ኔፊ ፲፩ ፡ ፴፰–፴፱ ። ቅ.መ.መ. አለት ።
ሀ ቅ.መ.መ. ፅዮን ።
ለ ት. እና ቃ. ፳፩ ፡ ፱ ።
ሐ ቅ.መ.መ. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ።
መ ፲ ኔፊ ፳፯ ፡ ፲፯ ። ቅ.መ.መ. መፅናት ።
ሠ ቅ.መ.መ. የሰለስቲያል ክብር ።
ረ ኢሳ. ፶፪ ፡ ፯ ፤ ሞዛያ ፲፭ ፡ ፲፡–፲፫ ፤ ፲ ኔፊ ፳ ፡ ፵ ።

ራች የሚናገሩ፣ በተራሮች ላይ እንዴት ያማሩ ይሆናሉ።

፴፯ እናም እንዲህ ሆነ የወንድሞቼ ዘር ቅሪት የሆኑትን እናም ደግሞ ከአይሁድ አንደበት የወጣው ᵐየእግዚአብሔር በግ መጽሐፍን፣ ይህም ᵃለወንድሞቼ ዘር ቅሪት ከአህዛብ እንደመጣ ተመለከትኩ።

፴፱ እናም ይህም ለእነሱ ከመጣ በኋላ፣ አህዛብን፣ የወንድሞቼን ዘር ቅሪት፣ ደግሞም በምድር ገፅ ላይ የተበተኑት አይሁዶችን ሁሉ፣ የነቢያት መዝገቦችና የበጉ አስራ ሁለት ሐዋርያት ᵐእውነት እንደሆኑ ᵃለማሳመን በበጉ ኃይል ከአህዛብ ለእነሱ ሌሎች ᵐመጽሐፎች ሲመጡ አየሁ።

፴ እናም መልአኩ እንዲህ ሲል ተናገረኝ—ከአህዛቦች መካከል ያየሀቸው እነዚህ ᵐየመጨረሻው መዝገቦች፣ ከበጉ አስራ ሁለት ሐዋርያት የሆኑትን ᵃየመጀመሪያውን ᵐእውነት ያረጋግጣሉ፤ ከእነርሱ የተወሰዱትን ግልፅና የከበሩ ነገሮች እንዲታወቁም ያደርጋሉ፤ የእግዚአብሔርም በግ የዘለአለማዊው አባት ልጅና ᵐየአለም አዳኝ እንደሆነ፣ እንዲሁም ሁሉም ሰዎች ወደ እርሱ መምጣት እንዳለባቸው ወይም መዳን እንደማይችሉ ለሁሉም ነገዶች፣ ቋንቋዎችና ህዝቦች እንዲታወቁ ያደርጋሉ።

፴፩ እናም እነርሱ በበጉ በተመሰረቱት ቃላት መሰረት መምጣት አለባቸው፣ የበጉም ቃላት በአንተ ዘሮች መዝገቦች ውስጥ፣ እንዲሁም በአስራ ሉለቱ የበጉ ሐዋሪያት መዝገቦች ውስጥ ይታወቃሉ፤ ስለዚህ ሁለቱም ᵐበአንድነት ይመሰረታሉ፤ በምድር ላይ ሁሉ ᵃአንድ አምላክ እና አንድ ᵐእረኛ አለና።

፴፪ እናም ለሁሉም ሀገር፣ ᵐለአይሁዶችና ደግሞ ለአህዛብ፣ እራሱን የሚገልጥበት ጊዜ ይመጣል፣ እርሱም እራሱን ለአይሁዶችና ደግሞ ለአህዛብ ከገለፀ በኋላ እራሱን ለአህዛብና ደግሞ ለአይሁዶች ይገልፃል፣ እንዲሁም ᵃየኋለኞች ፊተኞች፣ ᵐፊተኞችም ኋለኞች ይሆናሉ።

ምዕራፍ ፲፭

መልአክ በአህዛብ ላይ ስለሚመጡት በረከቶችና እርግማን ለኔፊ ነገረው—ሁለት ቤተክርስቲያናት ብቻ አሉ፥ የእግዚአብሔር በግ ቤተክርስቲያን እና የዲያብሎስ ቤተክርስቲያን—በሁሉም ሀገሮች ውስጥ የእግዚአብሔር ቅዱሳን በታላቋና በርኩሰት ቤተክርስቲያን ተሰድደዋል—ሐዋርያው ዮሐንስ ስለ ዓለም መጨረሻ ይፅፋል። ከ፲፮–፳፱ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ይሆናል፣ የእግዚአብሔርን በግ ᵐየማሰናከያውን ድንጋይ በመውሰድ እራሱን በቃል፣ ደግሞም ᵃበሀይል፣ እንዲሁም በስራው፣ ለእነርሱ በሚገልፅበት ጊዜ ᵐአህዛብ እርሱን ካዳመጡ—

፪ እናም በአባትህ ዘሮች መካከል እንዲቆጠሩ ዘንድ በእግዚአብሔር በግ ላይ ልባቸውን ካላጠጠሩ፣ አዎን፣ ከእስራኤልም ቤት መካከልም ᵐይቆጠራሉ፤ እነርሱም በቃል

፴፯ ᵐ ፩ ኔፊ ፲፫፡፳፫፣
፪ ኔፊ ፳፱፡፱–፲፣
ᵃ ሞር. ፭፡፲፭።
፴፱ ᵐ ፩ ኔፊ ፲፡፡ ፴፡
ᵃ ሕዝ. ፴፯፡፲፭–፳፣
፪ ኔፊ ፫፡፲፭–፲፪።
ᵐ ቅ.መ.መ. ቅዱሳት መጻህፍት—እንደሚመጡ የተተነበዩ ቅዱሣት መጻህፍት።
፴ ᵐ ፪ ኔፊ ፳፯፡፲፭–፲፯፣
፳፱፡፲፪።
ᵃ ቅ.መ.መ. መፅሐፈ ሞርሞን።
ᵐ ቅ.መ.መ. መፅሐፍ ቅዱስ።
ᵐ ሞር. ፯፡፳–፴።
ᵐ ደግሞም የመፅሐፈ ሞርሞን የርዕስ ገፅን ተመልከቱ።
ᵐ ሙሴ ፩፡፮።
፴፩ ᵐ ሕዝ. ፴፯፡፲፯።
ᵃ ዘዳግ. ፮፡፬፣
ዮሐ. ፲፯፡፳፩–፳፫፣
፪ ኔፊ ፴፩፡፳፩።
ᵐ ቅ.መ.መ. መልካሙ እረኛ።
፴፪ ᵐ ት. እና ቃ. ፯፡፳–፴፣
፲፯፡፴፣ ፲፲፪፡፬።
ᵃ ያዕቆ. ፭፡፳፣ ፲፣
ᵐ ሉቃ. ፲፣ ፴፣
፩ ኔፊ ፲፭፡ ፲፣–፳።
ᵐ ᵐ ኢሳ. ፶፯፡ ፲፬፣
፩ ኔፊ ፲፣ ፡፳፣ ፴፬፣
፪ ኔፊ ፳፯፡ ፳።
ᵃ ፩ ተሰ. ፩፡ ፭፣
፩ ኔፊ ፲፬፡ ፲፬፣
ያዕቆ. ፯፡ ፪–፣።
ᵐ ᵐ ኔፊ ፲፯፡ ፯–፲፣።
ቅ.መ.መ. አህዛቦች።
፪ ᵐ ገላ. ፣፡ ፯፣ ፳፬፣
፪ ኔፊ ፣፡ ፲፳–፲፬፣
ᵐ ኔፊ ፲፯፡ ፲ᵐ፣
ᵐ ᵐ ኔፊ ፲፯፡ ᵐ፣
፳፩፡ ፯፣ ፳፪፣
አብር. ፪፡ ፱–፲፩።

ኪዳኑ ምድር ለዘለአለም ^የተባረኩ ህዝቦች ይሆናሉ፤ ከዚህ ወዲያም ወደምርኮ አይ መጡም፤ ከዚህም ወዲያ የእስራኤል ቤት ከሌሎች ህዝቦች ጋር አይደባለቁም።

፲ እናም በዲያብሎስና በልጆቹ በተቋቋመው በታላቋና በርኩሰቱ ቤተክርስቲያን የሰዎችን ነፍስ ወደ ሲኦል ይወስድበት ዘንድ የተቆፈረው ትልቁ ^ጉድጓድ—አዎን፣ ሰዎችን ለማጥፋት የተቆፈረው ታላቁ ጉድጓድ በፍጹም እንዲጠፉ ዘንድ በቆፈሩት ይሞላል ይላል የእግዚአብሔር በግ፤ መጨረሻ ወደሌለው ወደዚያ ^ሲኦል ካልጣላቸው በሰተቀር፣ የነፍስ መጥፋት አይደለም።

፲፩ እነሆም ይህ በዲያብሎስ ምርኮ፣ እናም ደግሞ በእግዚአብሔር ፍትህ መሰረት በእርሱ ፊት ኃጢያትንና እርኩሰትን ባደረጉት ላይ ሁሉ ነው።

፲፪ እናም እንዲህ ሆነ መልአክ እንዲህ ብሎ ለእኔ ለኔፊ ተናገረኝ—አንተ አህዛብ ንስሀ ከገቡ መልካም እንደሚሆንላቸው አይ ተሀል፣ አንተም ደግሞ ጌታ የእስራኤልን ቤት በተመለከተ የገባውን ቃል ኪዳን ታውቃለህ፣ እናም ማንም ^ንስሀ የማይገባ መጥፋት እንዳለበት ሰምተሀል።

፲፫ ስለዚህ፣ በእግዚአብሔር በግ ላይ ልባቸውን ቢያጠጥሩ ለአህዛብ ^ወየው።

፲፬ በአንድም መንገድ ይሁን በሌላ ዘለዓለማዊ በሚሆነው ስራ—እነርሱ ሰላም ንና ^ዘለዓለማዊ ህይወትን እንዲመርጡ፣ ወይም እነርሱን ልባቸው በማጣጠርና አዕምሮአቸው በማሳወር ወደ ምርኮ፣ እናም ደግሞ እኔ በተናገርኩት በዲያብሎስ ^ምርኮ መሰረት እነርሱን ወደጊዜያዊና መንፈሳዊ ጥፋት እንዲሰጡ በሚያደርገው ስራ፣ እኔ ታላቅና ^ድንቅ ስራን በሰው ልጆች መካከል የምሰራበት ጊዜው ይመጣል፣ ይላል የእግዚአብሔር በግ።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ መልአኩ እነዚህን ቃላት ከተናገረ በኋላ እንዲህ አለኝ፥ አብ ለእስራኤል ቤት የገባውን ^ቃልኪዳኖች ታስታውሳለህን? እኔም አዎን አልኩት።

፲፮ እናም እንዲህ ሆነ፣ እንዲህ አለኝ—የኃጢኣት እናትን፣ መስራቿ ^ዲያብሎስ የሆነውን ታላቋና የርኩሰት እናት የሆነችው የርኩሰት ቤተክርስቲያን ተመልከት።

፲፯ እርሱም እንዲህ አለኝ—እነሆ ^ሁለት ቤተክርስቲያናት ብቻ አሉ፤ አንዷ የእግዚአብሔር በግ ቤተክርስቲያን ናት፣ ^ሌላዋም የዲያብሎስ ቤተክርስቲያን ናት፤ ስለዚህ ማንኛውም የእግዚአብሔር በግ ቤተክርስቲያን አባል ያልሆነ የርኩሰት እናት ከሆነችው የታላቂቷ ቤተክርስቲያን አባል ይሆናል፤ እናም እርሷ የምድር ሁሉ ^ኃጋለሞታ ነች።

፲፰ እናም እንዲህ ሆነ የምድርን ሁሉ ኃጋለሞታ አየሁና ተመለከትኩ፣ እርሷም በብዙ ^ውኃዎች ላይ ተቀምጣ ነበር፤ እናም ^እርሷ በሁሉም ሀገሮች፣ ነገዶች፣ ቋንቋዎችና ህዝቦች መካከል በምድር ላይ ሁሉ ትገዛለች።

፲፱ እናም እንዲህ ሆነ የእግዚአብሔር በግ ቤተክርስቲያንን ተመለከትኩ፣ እናም በብዙ ውኃዎች ላይ በተቀመጠችው ኃጋለሞታ ክፋትና ርኩሰቶች ምክንያት ቁጥሯ ^ጥቂት ነበሩ፤ ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ቅዱሳን የሆኑት የበጉ ቤተክርስቲ

፲፩ ለ ፲፩ ኔፊ ፲፣ ፲፡ ፳–፲፩፤ ፲፫ ኔፊ ፲፡ ፲–፲፭፤ ፲፭ ኔፊ ፲፣ ፡ ፳፣ ፳፪።
፲፫ ሀ ፩ ኔፊ ፳፪፡ ፲፡ ፡ ት. እና ቃ. ፲፱፡ ፳፭።
ለ ቅ.መ.መ. ሲያል፤ ኩነኔ።
፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣ ንስሀ መግባት።
፲፮ ሀ ፩ ኔፊ ፳፳፡ ፴፪።
፲፯ ሀ ፩ ኔፊ ፪፡ ፳፯–፳፱፤ አልማ ፲፪፡ ፱–፲፩።
ለ ቅ.መ.መ. የዘለዓለም ህይወት።
ሐ ኢሳ. ፳፱፡ ፲፡ ፩ ኔፊ ፳፪፡ ፳፡ ፪ ኔፊ ፳፯፡ ፳፯–፳፡ ፳፱፡ ፩–፪፤ ት. እና ቃ. ፡ ፩። ቅ.መ.መ. የወንጌል ዳግም መመለስ።
፲፱ ሀ ቅ.መ.መ. የአብርሐም ቃል ኪዳን።
፳ ሀ ፩ ኔፊ ፲፭፡ ፴፭፤ ት. እና ቃ. ፩፡ ፴፭። ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
፲ ሀ ፩ ኔፊ ፳፪፡ ፳፫።
ለ ፩ ኔፊ ፲፫፡ ፡–፣ ፳፯።
ሐ ራዕ. ፲፯፡ ፭፣ ፲፭፤ ፪ ኔፊ ፲፡ ፲፯።
፲፩ ሀ ኤር. ፶፩፡ ፲፫፤ ራዕ. ፲፯፡ ፲፭።
ለ ት. እና ቃ. ፴፭፡ ፲፩።
፲፪ ሀ ማቴ. ፯፡ ፲፡ ፲፡ ፣ ፲፡ ፲፡ ት. እና ቃ. ፲፴፭፡ ፳፯።

ያን አባላቶቿም ደግሞ ^በምድር ገፅ ላይ ሁሉ እንደነበሩ ተመለከትኩ፤ እናም በተ መለከትኳት ትልቅ ጋለሞታ ክፋት ምክ ንያት በምድር ገፅ ላይ የሚገዙት ቦታዎች ትንሽ ነበሩ።

፲፫ እናም እንዲህ ሆነ ታላቂቱ የርኩሰት እናት ከእግዚአብሔር በግ ጋር *በመዋጋት በምድር ገፅ ላይ ሁሉ ከሁሉም የአህዛብ ሀገ ሮች መካከል ብዛትን በአንድ ላይ እንደሰበ ሰበች ተመለከትኩ።

፲፬ እናም እንዲህ ሆነ እኔ ኔፊ በበጉ ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳንና በምድር ገፅ ላይ ሁሉ በተበተኑት የጌታ የቃል ኪዳን ህዝቦች ላይ የእግዚአብሔር በግ ኃይል ሲወርድ ተመ ለከትኩ፤ እነርሱም ፅድቅንና የእግዚአብ ሔርን *ኃይል በታላቅ ክብር የታጠቁ ነበሩ።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ የእግዚአብሔር ቁጣ በታላቋና በርኩሰት ቤተክርስቲያን ላይ *ፈሰሰ በዚያም በምድር ባሉ ^ሀገሮ ችና ነገዶች ሁሉ መካከል ጦርነቶችና የጦ ርነት ወሬዎች እንደነበሩ ተመለከትኩ።

፲፮ እናም *ጦርነቶችና የጦርነት ወሬዎች በሁሉም የርኩሰት እናት በሆነችው በሚ መሩት ሀገሮች መካከል ሲጀመር መልአኩ እንዲህ ሲል ተናገረኝ—እነሆ የእግዚአብ ሔር ቁጣ በጋለሞታዎች እናት ላይ ነው፣ እናም እነሆ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ትመለ ከታለህ—

፲፯ እናም የእግዚአብሔር *ቁጣ በጋለሞ ታዎች እናት፣ በምድር ሁሉ ታላቋና በተ ረኮሰች በዲያብሎስ በተመሰረተች ቤተክ ርስቲያን ላይ የሚፈሰበት ^ቀን ሲመጣ፣ ከዚያም በእዚያ ቀን የእስራኤል ቤት ለሆ ኑት ለህዝበቹ የገባውን ^ቃል ኪዳኖች ለማ ሟላት መንገድን በማዘጋጀት የአብ ™ስራ ይጀምራል።

፲፰ እናም እንዲህ ሆነ መልአኩ እንዲህ ሲል ተናገረኝ፣ ተመልከት!

፲፱ እናም ተመለከትኩና፣ አንድ ሰው አየሁ፣ እርሱም ነጭ ካባ ለብሶ ነበር።

፳ እናም መልአኩ አለኝ፣ እነሆ ከበጉ አስራ ሁለት ሐዋርያት *አንዱ።

፳፩ እነሆ እርሱ ከእነዚህ ነገሮች ቀሪዎ ቹን ይመለከታል፣ እንዲሁም ይፅፋል፣ አዎን፣ ደግሞም ብዙ ነገሮችን ተመልክ ቶም ይፅፋል።

፳፪ እናም ደግሞ እርሱ ስለ ዓለም ፍፃሜ ይፅፋል።

፳፫ ስለዚህ እርሱ የሚፅፋቸው ነገሮች ትክክልና እውነት ናቸው፤ እናም እነሆ እነርሱ ከአይሁድ አፍ ሲወጡ በተመለከ ትካቸው *መፅሐፉ ውስጥ የፃፉት ናቸው፣ ከአይሁድም አፍ በወጡበት ጊዜ ወይም መፅሐፉ በአይሁድ አፍ በወጡበት ጊዜ የተፃፉት ነገሮች ግልፅና የጠሩ እንዲሁም እጅግ ^የከበሩና ለሰዎች ሁሉ ለመረዳት ቀላል ነበሩ።

፳፬ እናም እነሆ ይህ የበጉ *ሐዋርያ የሚ ፅፋቸው ነገሮች አንተ ያየሀቸው ብዙ ነገ ሮች ናቸው፤ እነሆ ቀሪዎቹን አንተም ትመ ለከታለህ።

፳፭ ነገር ግን ከዚህ በኋላ የምታያቸውን ነገሮች እንዳትፅፍ፤ የእግዚአብሔር በግ ሐዋርያ የሆነው *መፃፍ እንዳለበት ጌታ እግዚአብሔር ሾሞታልና።

፳፮ እናም ደግሞ ለነበሩም ሌሎች ሁሉንም ነገሮች አሳይቶአቸዋል፣ እነርሱም ፅፈዋቸ ዋል፤ እንዲሁም በጉ ውስጥ ካሉት እውነታ

፲፪ *ለ ት.እና ቃ. ፣፡ ፲፩።
፲፫ *ሀ ራዕ. ፲፯፡ ፩–፮፣ ፲፰፡ ፳፬፣ ፩ ኔፊ ፲፫፡ ፭፣ ት.እና ቃ. ፻ሺ፲፡ ፯–፰።
፲፬ *ሀ ያዕቆ. ፮፡ ፪፣ ት.እና ቃ. ፴፰፡ ፴፪–፴፰።
፲፭ *ሀ ት.እና ቃ. ፩፡ ፲፫–፲፬።
*ለ ማር. ፲፫፡ ፰፣ ት.እና ቃ. ፹፯፡ ፮።
፲፯ *ሀ ፩ ኔፊ ፳፪፡ ፲፫–፲፬፣ ሞር. ፰፡ ፴።
፲፱ *ሀ ፩ ኔፊ ፳፪፡ ፲፭–፲፮።
*ለ ቅ.መ.መ. የመጨረሻ ቀናት፣ የኋለኛው ቀናት።
*ሐ ሞር. ፰፡ ፳፩፣ ፴፩።
ቅ.መ.መ. የአብርሐም ቃል ኪዳን።
*መ ፫ ኔፊ ፳፩፡ ፯፣ ፳–፳፬። ቅ.መ.መ. የወንጌል ዳግም መመለስ።
፳ *ሀ ራዕ. ፩፡ ፩–፫፣ ፩ ኔፊ ፲፡ ፳፯።
፳፩ *ሀ ፩ ኔፊ ፲፡ ፳–፳፡ ሞር. ፰፡ ፴፫። *ለ ፩ ኔፊ ፲፡ ፳፰–፴፪።
፳፪ *ሀ ኤተር ፪፡ ፲፯።
፳፫ *ሀ ዮሐ. ፳፡ ፴–፴፩፣ ራዕ. ፩፡ ፲፱።

መሰረት፣ ጌታ በፈቀደ ጊዜ ለእስራኤል ቤት በንፅህና ይመጡ ዘንድ ሀታትመዋል።

፳፯ እናም እኔ ኔፊ በመልአኩ ቃል መሰረት የበጉ ሐዋርያ ስም ሀዮሐንስ መሆኑን ሰምቼአለሁም እመሰክራለሁም።

፳፰ እናም እነሆ እኔ ኔፊ፣ የተቀሩትን ያየሁአቸውንና የሰማሁአቸውን ነገሮች እንዳልፅፍ ተከልክዬአለሁ፣ ስለዚህ እኔ የፃፍኳቸው ነገሮች በቂ ናቸው፤ እናም እኔ ካየሁአቸው ጥቂት ነገሮች ብቻ ጽፌአለሁ።

፳፱ እኔም ሀአባቴ ያያቸውን ነገሮች እንዳየሁ እመሰክራለሁ፣ እናም የጌታ መልአክ እንዳውቃቸው አደረገኝ።

፴ አሁንም እኔ በመንፈስ በተወሰድኩ ጊዜ ስላየኋቸው ነገሮች መናገሬን አቆማለሁ፤ እናም ምንም እንኳን ያየሁአቸው ነገሮች ሁሉ ባይፃፉም የፃፍኳቸው ነገሮች ሀእውነት ናቸው፣ እናም ይህ ነው። አሜን።

ምዕራፍ ፲፭

የሌሂ ዘሮች በኋለኛው ቀናት ከአህዛብ ወንጌልን ይቀበላሉ—የእስራኤልም መሰባሰብ የተፈጥሮ ቅርንጫፎቹ መልሰው እንደሚጣበቁ የወይራ ዛፍ ጋር ይመሳሰላል—ኔፊ የህይወት ዛፍን ራዕይ ተረጎመ እናም እግዚአብሔር ኃጢአተኛን ከፃድቅ ስለሚለያይበት ፍትህ ተናገረ። ከ፮፻–፭፻፺፪ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ እኔ፣ ኔፊ፣ በመንፈስ ከተወሰድኩና እነዚህን ሁሉ ነገሮች ካየሁ በኋላ ወደአባቴ ድንኳን ተመለስኩ።

፪ እናም እንዲህ ሆነ ወንድሞቼን ተመለከትኩ፣ እነርሱም አባቴ ለእነርሱ የተናገራቸውን ነገሮች በተመለከተ እርስ በእርሳቸው እየተከራከሩ ነበር።

፫ ሰው ጌታን ካልጠየቀ በቀር ሀለመረዳት የሚያስቸግሩ ብዙ ታላቅ ነገሮችንም ነበር በእውነት ለእነርሱ ነግሯቸዋልና፤ እነርሱ በልቦቻቸው መጠጠር የተነሳ ማድረግ እንደነበረባቸው ወደጌታ አልተመለከቱም።

፬ እናም አሁን እኔ ኔፊ በልባቸው ጠጣርነት፣ ደግሞም ባየሁአቸው ነገሮች ምክንያትና በሰዎች ልጆች ታላቅ ኃጢያት ምክንያት ሊወገዱ በማይችሉ መምጣት እንዳለባቸው ስላወቅሁ እጅግ አዘንኩ።

፭ እናም እንዲህ ሆነ በራሴ ሀዘን ምክንያት ተሸነፍኩ፣ ምክንያቱም ውድቀታቸው እንዴት እንደሚሆን ስለተመለከትኩ፣ በህዝቤ ሀጥፋት ምክንያት የእኔ ለህዘን ከማንኛውም በላይ ታላቅ እንደነበር ተሰማኝ።

፮ እናም እንዲህ ሆነ ሀጥንካሬን ካገኘሁ በኋላ ወንድሞቼን የክርክራቸው ምክንያት ምን እንደነበር ለማወቅ ተናገርኳቸው።

፯ እናም እነሆ የተፈጥሮ ወይራ ዛፍን ቅርንጫፎችና፣ ደግሞም አህዛብን በተመለከተ አባታችን የተናገራቸውን ነገሮች ለመረዳት አንችልም አሉ።

፰ እናም እንዲህ አልኳቸው፥ እናንተ ጌታን ሀጠይቃችኋልን?

፱ እናም እንዲህ አሉኝ—አልጠየቅንም፣ ምክንያቱም ጌታ እኛን እንዲህ ያሉ ነገሮችን አያሳውቀንም።

፲ እነሆ እነርሱን አልኳቸው—እንዴት ነው እናንተ የጌታን ትዕዛዝ የማትጠብቁት? እንዴት ነው በልባችሁ ሀጠጣርነት የተነሳ የምትጠፉት?

፲፩ ጌታ የተናገራቸውን ነገሮች አታስታውሱምን?—ልባችሁን ባታጠጥሩ እናም መልስ እንደምታገኙም በማመን ትዕዛዛቴን ለመጠበቅ በመትጋት በእምነት ሀብትጠ

፳፮ ሀ ፪ ኔፊ ፳፯፥፯–፳፫፤
ኤተር ፫፥፳፩–፳፯፤
፬፥፬–፯፤
ት. እና ቃ. ፴፭፥፲፰፤
ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፳፭።
፳፯ ሀ ራዕ. ፩፥፩–፫።
፳፱ ሀ ፩ ኔፊ ፰።
፴ ሀ ፪ ኔፊ ፴፫፥፲–፲፬።

፲፭ ፫ ሀ ፩ ቆሮ. ፪፥፲–፲፪፤ አልማ
፲፪፥፱–፲፩።
፭ ሀ ኢኖስ ፩፥፲፫፤
ሞር. ፮፥፩።
ለ ቅ.መ.መ. ጭንቀት።
፮ ሀ ሙሴ ፩፥፲፤
ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፳፤ ፵፰።
፰ ሀ ሞዛያ ፳፮፥፲፫፤
አልማ ፵፥፫።
ቅ.መ.መ. ጸሎት።
፲ ሀ ቅ.መ.መ. ክህደት።
፲፩ ሀ ያዕ. ፩፥፭–፮፤
ኢኖስ ፩፥፲፭፤
ሞሮኒ ፯፥፳፮፤
ት. እና ቃ. ፲፰፥፲፰።
ቅ.መ.መ. ለምን።

ይቁኝ፣ በእርግጥ እነዚህ ነገሮች ለእናንተ ግልፅ ይሆናሉ።

፲፪ እነሆ እላችኋለሁ የእስራኤል ቤት ከወ ይራው ዛፍ ጋር የተመሳሰለው በአባታችን ውስጥ በነበረው በጌታ መንፈስ ነበር፤ እናም እነሆ እኛ ከእስራኤል ቤት የተሰበርን አይ ደለንምን? ደግሞስ የእስራኤል ቤት *ሀቅር ንጫፎች አይደለንምን?

፲፫ እናም አሁን በአህዛብ ሙላት የተ ፈጥሮ ቅርንጫፎች መጣበቅ በተመለ ከተ አባታችን የተናገረው ነገር በኋለኛው ቀናት ዘሮቻችን እምነት በማጣት *ሲመ ነምኑ፣ አዎን፣ ለብዙ ዓመታት፣ እንዲ ሁም *መሲሁ ለሰዎች ልጆች እራሱን ከገ ለፀ ከብዙ ትውልዶች በኋላ፣ ከዚያም የመ ሲህ *ሐወንጌል ሙሉነት *ለአህዛብ፣ ከአ ህዛብም ወደ ዘሮቻችን ቅሪት ይመጣል—

፲፬ እናም በዚያ ቀን *የዘሮቻችን ቅሪት ከእስራኤል ቤት መሆናቸውን፣ እነርሱም የጌታ *የቃል ኪዳን ህዝቦች መሆናቸውን ያውቃሉ፤ ከዚያም እነርሱ ቅድመ አባቶ ቻቸው ወደማወቅ፣ ደግሞም በእርሱ አባ ቶቻቸው የተማሩትን የመድኃኒታቸውን ወንጌል ያውቃሉም፣ *ሐለእውቀትም ይደ ርሳሉ፤ ስለዚህ እነርሱ ወደ መድኃኒታቸው እውቀትና፣ ወደእርሱ እንዴት እንደሚመ ጡና እንደሚድኑ ያውቁ ዘንድ ወደ ትምህ ርቱ እያንዳንዱ ነጠቦች በእውቀትም ይደ ርሳሉ።

፲፭ በዚያም ቀን አይደሰቱምን እና *አለ ታቸውና አዳኛቸው ለሆነው ለዘለአለማዊው አምላክ ምስጋናን አያቀርቡምን? አዎን፣ በዚያ ቀን እነርሱ ከእውነተኛው *ወይን ጥንካሬንና ጥቅም አያገኙምን? አዎን፣ ወደ እውነተኛው የእግዚአብሔር በረት አይመ ጡምን?

፲፮ እነሆ እላችኋለሁ፣ አዎን፣ እነርሱ በድጋሚ በእስራኤል ቤት መካከል ይታ ወሳሉ፤ ምክንያቱም የወይራ ዛፍ የተፈጥሮ ቅርንጫፎች በመሆናቸው ከእውነተኛው የወይራ ዛፍ ጋር *ይጣበቃሉና።

፲፯ አባታችንም ይህን ማለቱ ነው፤ እንዲ ሁም በአህዛብ እስከሚበተኑም ድረስ አይ ሆንም ማለቱ ነው፤ እና ማለቱም ጌታ ለአ ህዛብ ኃይሉን ያሳያቸው ዘንድ፣ ይህም በአ ህዛቦች አማካኝነት ይመጣል፣ ምክንያቱም በአይሁዶች ወይም እስራኤል ቤት *ተቀባ ይነት አያገኝምና።

፲፰ ስለዚህ አባታችን ስለ እኛ ዘር ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ስለ እስራኤል ቤት ሁሉ ተናግሯል፣ በኋለኛው ቀን የሚፈፀመውን ቃል ኪዳን አመልክቷል፤ ይኸውም ጌታ ለአባታችን አብርሃም እንዲህ በማለት የገ ባው ቃል ኪዳን ነው፡ *በዘርህ የምድር ወገ ኖች ሁሉ ይባረካሉ።

፲፱ እናም እንዲህ ሆነ እኔ ኔፊ ለእነርሱ እነዚህን ነገሮች በተመለከተ ብዙ ተናገ ርኩ፤ አዎን፣ በኋለኛው ቀናት ስለአይሁ ዶች *በዳግም መመለስን በሚመለከትም ለእነርሱ ተናገርኩ።

፳ እናም ለእነርሱ ስለ አይሁዶች ወይም ስለ እስራኤል ቤት መመለስ *ኢሳይያስ የተናገረውን ቃል፣ እንዲሁም እነርሱ ከተ መለሱ በኋላ ከሌሎች ህዝቦች ጋር እንደ ማይቀላቀሉ፣ በድጋሚም እንደማይበተኑ አስረዳኋቸው። እናም እንዲህ ሆነ ለወን

፲፪ *ሀ* ዘፍጥ. ፴፱፡፲፭–፳፮፤ ፩ ኔፊ ፲፡፲፪–፲፬፤ ፲፱፡፳፬። ቅ.መ.መ. ሌሂ፣ የኔፊ አባት።

፲፫ *ሀ* ፩ ኔፊ ፲፪፡፳፪–፳፫፤ ፪ ኔፊ ፳፯፡፲፭። *ለ* ቅ.መ.መ. መሲህ። *ሐ* ቅ.መ.መ. ወንጌል። *መ* ፩ ኔፊ ፲፫፡፴፪፣ ፳፪፡፭–፲፤ ት.እና ቃ. ፲፱፡፲። ቅ.መ.መ. አህዛቦች።

፲፬ *ሀ* ፪ ኔፊ ፲፡፪፤ ፫ ኔፊ ፲፡፲–፲፬፤ ፲፱፡፳–፳፩።

፲፭ *ሀ* ቅ.መ.መ. አለት።

፲፮ ኔፊ ፭፡፳፩–፳፯፤ ፳፭፡፪–፲።

ለ ቅ.መ.መ. የአብርሐም ቃል ኪዳን።

ሐ ፪ ኔፊ ፲፡፲፪፣ ፴፡፭፤ ሞር. ፯፡፭፣ ፱–፲፣ ት.እና ቃ. ፲፡፲፯–፳። ደግሞም የመፅሐፈ ሞርሞን የርዕስ ገፅን ተመልከቱ።

፲፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. አለት።

ለ ዘፍጥ. ፴፱፡፲፭፣ ዮሐ. ፲፭፡፩።

፲፯ *ሀ* ያዕቆ. ፭፡፳–፳፰። ፲፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. መሰቀል።

፲፰ *ሀ* ዘፍጥ. ፲፪፡፩–፲፣ አብር. ፪፡፯–፲፩።

፲፱ *ሀ* ፩ ኔፊ ፲፱፡፲፭። ቅ.መ.መ. እስራኤል— የእስራኤል መሰብሰብ።

፳ *ሀ* ፩ ኔፊ ፲፱፡፳፣ ፳፲።

ድሞቼ እንዲረጋጉና በጌታ ፊት እራሳቸ
ውን ^ትሁት እንዲያደርጉ ብዙ ቃል ነገ
ርኳቸው።

፳፩ እናም እንዲህ ሆነ በድጋሚ እንዲህ
ሲሉ ተናገሩኝ—አባታችን በህልሙ ያየው
ይህ ነገር ምን ማለት ነው? እርሱ ያየው
ᵛዛፍስ ምን ማለት ነው?

፳፪ እናም አልኳቸው—እሱ ᵛየህይወት
ዛፍ ምልክት ነበር።

፳፫ እናም እንዲህ አሉኝ—ወደዛፉ የሚ
መራን አባታችን ያየው ᵛየብረት በትር ምን
ማለት ነው?

፳፬ ይህም የእግዚአብሔር ᵛቃል ነበር
አልኳቸው፤ እናም የእግዚአብሔርን ቃል
የሚሰሙ ሁሉና፣ እርሱን አጥብቆ ^የያዘ
በፍፁም አይጠፋም፤ ^ፈተናዎችና ᵛየጠ
ላት ክፉ ᵛፍላፃ እነርሱን ወደጥፋት ለመው
ሰድ በማሳወር ሊያሸንፏቸው አይችሉም።

፳፭ ስለዚህ እኔ ኔፊ የጌታን ቃል በጥብቅ
ᵛእንዲያዳምጡ አበረታታኋቸው፤ አዎን፣
በውስጤ ባለው ኃይል ሁሉ እናም ባለኝ
ችሎታ ሁሉ የጌታን ቃል በጥብቅ ያዳ
ምጡ ዘንድ እንዲሁም በሁሉም ነገሮች
ሁል ጊዜ ትዕዛዛቱን በመጠበቅ እንዲያስ
ታውሱት መከርኳቸው።

፳፮ እናም ተናገሩኝ—አባታችን የተመለ
ከተው ᵛየወንዙ ውሃ ምን ማለት ነው?

፳፯ እናም አባቴ ያየው ᵛውኃ ^ርኩሱን
ነገር ነበር አልኳቸው፤ አእምሮውም ሌሎች
ነገሮችን በማሰብ የተሞላ ስለነበር የውሀውን
ርኩስነት ልብ አላለውም ነበር።

፳፰ እናም ኃጢአተኞችን ከህይወት ዛፍ፣
እናም ደግሞ ከእግዚአብሔር ቅዱሳን የሚ
ለያይ አሰቃቂ ᵛገደል ነበር አልኳቸው።

፳፱ እናም ይህ የአሰቃቂው ᵛሲኦል ምል
ክት ነበር፣ እርሱም መልአኩ እንደነገረኝ
ለኃጢአተኞች የተዘጋጀ ነበር አልኳቸው።

፴ እናም አባታችን የእግዚእብሔር
ᵛፍትህ ደግሞ ኃጢአተኞችን ከፃድቃን
እንደሚለይ እንዳየ፣ ድምቀቱም በመቀ
ጠል ለዘለዓለም ወደ እግዚአብሔር እንደ
ሚመጣና መጨረሻ እንደሌለው ልክ እን
ደነበልባል እሳት ደምቆ እንደነበር ነገር
ኳቸው።

፴፩ እናም እነርሱ ለእኔ አሉኝ—ይህ ነገር
በምድር ᵛየሙከራ ጊዜያችን በሚች የሰው
ነታችን ስቃይ ማለት ነው፣ ወይስ ይህ ከጊ
ዜያዊው ሰውነት ^ሞተ በኋላ የመጨረሻው
የነፍስ ሁኔታ ማለት ነው፣ ወይስ የሚናገ
ረው ነገር ጊዜያዊ ስለሆኑት ነገሮች ነው?

፴፪ እናም እንዲህ ሆነ እንዲህ አልኳ
ቸው—ይህ ለጊዜያዊና ለመንፈሳዊ ነገሮች
ምልክት ነበር፣ በስራዎቻቸው አዎን፣ እን
ዲሁም በሙከራ ጊዜያቸው በሚች ሰውነ
ታቸው በተደረጉት ᵛስራዎች፣ ሊፈረድባ
ቸው ይገባል።

፴፫ ስለዚህ በኃጢአታቸው ᵛየሚሞቱ
ከሆኑ፣ ከፅድቅነት ጋር ከተገናኙ መንፈሳዊ
ነገሮች ^መገለል ደግሞ ይገባቸዋል፤ ስለ
ዚህ ^በስራቸው ᵐእንዲፈረድባቸውም በእ
ግዚአብሔር ፊት ለመቆም መምጣት አለ
ባቸው፤ እናም ስራቸው የረከሰ ከሆነ እነ
ርሱም ᵛየረከሱ መሆን አለባቸው፤ የረከሱ
ከሆኑም ደግሞ በእግዚአብሔር መንግ

፳ ^ ፩ ኔፊ ፲፯፡፳፡ ፳፱፡ ፴፱።
፳፩ ^ ፩ ኔፊ ፳፡፲–፲፪።
፳፪ ^ ፩ ኔፊ ፲፩፡፱፡ ፳፩፤
ሙሴ ፫፡፱።
፳፫ ^ ፩ ኔፊ ፳፡፲፱–፳፩።
፳፬ ^ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር
ቃል።
^ ፩ ኔፊ ፳፡፴፤
፪ ኔፊ ፴፩፡፳።
^ ፩ ኔፊ ፳፡፳፫።
ቅ.መ.መ. መፈተን፣ ፈተና።
ᵐ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
ᵛ ኤፌ. ፮፡፲፮፤
ት. እና ቃ. ፫፡፳፤ ፳፯፡፲፯።
ᵛ ^ ት. እና ቃ. ፲፩፡፪፤ ፴፪፡፩፤
፹፭፡፴፫–፴፭።
ᵛ ^ ፩ ኔፊ ፳፡፲፫።
ᵛ ^ ፩ ኔፊ ፲፪፡፲፯።
^ ቅ.መ.መ. እድፍ፣
እድፍነት።
ᵛ ሉቃ. ፲፮፡፳፮፤
፩ ኔፊ ፲፪፡፲፳፤
፪ ኔፊ ፩፡፲፫።
ᵛ ቅ.መ.መ. ሲያል።
ᵛ ቅ.መ.መ. ፍትህ።
ᵛ አልማ ፲፪፡፳፬፤ ፴፪፡፲፤
ሔለ. ፲፫፡፴፳።
^ አልማ ፴፡፮፤ ፲፩–፲፬።
ᵛ ቅ.መ.መ. ስራዎች።
ᵛ ሞዛያ ፲፭፡፳፮፤
ሞሮኒ ፲፡፳፮።
^ አልማ ፲፪፡፲፪–፲፮፤ ፴፡፳፮።
ሐ ፫ ኔፊ ፳፮፡፳፫–፳፮።
መ ቅ.መ.መ. ፍርድ፣
የመጨረሻው።
ᵛ ፪ ኔፊ ፱፡፲፮፤
ት. እና ቃ. ፹፳፡፴፭።

ስት ውስጥ [ረ]መኖር አይችሉም፤ እንዲህም ከሆነ፣ የእግዚአብሔር መንግስት ደግሞ የረከሰ መሆን አለበት።

፴፬ ነገር ግን እነሆ እላችኋለሁ የእግዚአብሔር መንግስት [ሀ]የረከሰ አይደለም፣ እናም ማንኛውም እርኩስ ነገር ወደ እግዚአብሔር መንግስት ሊገባ አይችልም፤ ስለዚህ ርካሽ ለሆነው የተዘጋጀ የረከሰ ቦታ ሊኖር ይገባዋል።

፴፭ እናም የተዘጋጀ ቦታ፣ አዎን፣ እንዲሁም የተናገርኩት አሰቃቂው [ለ]ገሀነም አለ፣ የዚህም አዘጋጅም [ሐ]ዲያብሎስ ነው፤ ስለዚህ የሰዎች ነፍሶች የመጨረሻ ሁኔታ በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ መኖር፣ ወይም በተናገርኩት [መ]ፍትህ ምክንያት ወደውጭ መጣል ነው።

፴፮ ስለዚህ ኃጢአተኞች ከፃድቃን ጋር እናም ደግሞ ፍሬው እጅግ ያማረና ከሌሎች ፍሬዎች በላይ እጅግ [ሠ]ተፈላጊ ከሆነው [ረ]የህይወት ዛፍ ይለያሉ፤ አዎን፣ ይህ ከእግዚአብሔር [ሰ]ስጦታዎች ሁሉ [ሠ]የበለጠ ነው። እንደዚህም ነበር ለወንድሞቼ የተናገርኩት። አሜን።

ምዕራፍ ፲፮

ኃጢአተኞች እውነትን ለመቀበል አስቸጋሪ ይሆንባቸዋል—የሌሂ ወንዶች ልጆች የእስማኤልን ሴቶች ልጆች አገቡ—ሊያ ሆናው በምድረበዳ ውስጥ መንገዳቸውን መራቸው—ከጌታ የመጡ መልዕክቶች በተለያዩ ጊዜዎች በሊያሆናው ላይ ይፃፉ ነበር—እስማኤል ሞተ፣ ቤተሰቦቹም በስቃዮች ምክንያት አጉረመረሙ። ከ፯፻–፮፻፶፪ ዓ.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ እኔ ኔፊ፣ ወንድሞቼን ማነጋገር ከጨረስኩኝ በኋላ፣ እነሆ እነርሱ አንተ እኛ ልንጸናው ከምንችለው የበለጠ አስቸጋሪ ነገሮችን ነገርከን አሉኝ።

፪ እናም እንዲህ ሆነ እውነትን በተመለከተ ለኃጢአተኞች የተናገርኳቸው ነገሮች አስቸጋሪ እንደሆኑ አውቃለሁ አልኩ፤ እናም ፃድቃን ከጥፋት ነፃ መሆናቸውን ተናገርኩ፣ በመጨረሻውም ቀን ከእግዚአብሔር ጋር ከፍ እንደሚደረጉም መሰከርኩ፤ ስለዚህ [ሠ]ጥፋተኞች [ሀ]እውነትን ከባድም አድርገው ይወስዱታል፣ ከመሀከላቸው [ሐ]ይለያቸዋልና።

፫ እናም ወንድሞቼ፣ አሁን እናንተ ፃድቃን እንዲሁም እውነትን ለማዳመጥ ፈቃደኞች ብትሆኑ ኖሮ፣ በእግዚአብሔርም ፊት በቅንነት [መ]ትራመዱ ዘንድ በጥብቅ ከተከተላችሁት፣ በእውነት ምክንያት አታጉረመርሙም፣ ከባድ ነገሮችን በእኛ ላይ ትናገራለህ አትሉም።

፬ እናም እንዲህ ሆነ እኔ ኔፊ ወንድሞቼ የጌታን ትዕዛዛት እንዲጠብቁ በሙሉ ትጋት አበረታታኋቸው።

፭ እናም እንዲህ ሆነ፤ እነርሱ በፅድቅ ጎዳና ይራመዱ ዘንድ ደስታና ታላቅ ተስፋ እስኪኖረኝ ድረስ በጌታ ፊት እራሳቸውን [ሠ]ዝቅ አደረጉ።

፮ አሁን እነዚህ ነገሮች ሁሉ የተባሉትና የተደረጉት አባቴ ልሙኤል ብሎ በጠራው ሽለቆ በድንኳን በነበረበት ጊዜ ነው።

[ረ] መዝ. ፲፭፡ ፳፬፡ ፲–፴፤ አልማ ፲፩፡ ፴፮፣ ት. እና ቃ. ፍ፲፮፡ ፶–፷፣ ሙሴ ፮፡ ፶፯።
[ሀ] ቅ.መ.መ. እድፍ፣ እድፍነት።
[ለ] ፪ ኔፊ ፱፡ ፲፱፤ ሞዛያ ፳፯፡ ፳፯።
ቅ.መ.መ. ሲያል።
[ሐ] ፩ ኔፊ ፲፡ ፱፤ ት. እና ቃ. ፩፡ ፴፭።
[መ] ቅ.መ.መ. ፍትህ።
[ሠ] ፩ ኔፊ ፳፡ ፣–፲፪፤ አልማ ፴፪፡ ፶፪።
[ረ] ዘፍጥ. ፪፡ ፱፣ ፪ ኔፊ ፪፡ ፲፭።
[ሰ] ት. እና ቃ. ፲፡ ፮።
ቅ.መ.መ. የዘለዓለም ህይወት።
[ሠ] ት. እና ቃ. ፮፡ ፲፣ ፡
[ሀ] ፩ ኔፊ ፳፡ ፣–፲፪፤ ኢኖስ ፩፡ ፳፣ ሩት. ፲፡ ፣
[ለ] ፪ ኔፊ ፳፡ ፣–፲፪፤ ሩት. ፲፡ ፣
[ሐ] ፪ ኔፊ ፳፡ ፣–፲፪፤ ሩት. ፲፡ ፣
[መ] ፪ ኔፊ ፳፡ ፣–፲፪፤ ሩት. ፲፡ ፣
[ሠ] ፪ ኔፊ ፳፡ ፣–፲፪፤ ሩት. ፲፡ ፣
ቅ.መ.መ. በደል።
[ለ] ምሳ. ፲፭፡ ፣፣ ፪ ኔፊ ፩፡ ፳፯፣ ፱፡ ፴፣ ሩት. ፲፣ ፡ ፳፡ ፳–፳፮።
[ሐ] የሐዋ. ፭፡ ፴፣ ሞዛያ ፣፣ ፡ ፮።
[ሠ] ፣ ት. እና ቃ. ፭፡ ፳፭።
ቅ.መ.መ. መራመድ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መራመድ (መሄድ)።
[ረ] ፩ ኔፊ ፲፮፡ ፳፩፣ ፴፱፣ ፣፳፡ ፴።

፯ እናም እንዲህ ሆነ እኔ ኔፊ ከእስማኤል
ᵐሴቶች ልጆች አንዷን ᵃለማግባት ወሰ
ድኳት፤ እናም ደግሞ ወንድሞቼ የእስማ
ኤልን ሴቶች ልጆች ለማግባት ወሰዱ፤ ደግ
ሞም ᵇዞራም የእስማኤልን ትልቋን ሴት
ልጅ ለማግባት ወሰደ።

፰ አባቴም የተሰጡትን የጌታን ትዕዛዛት
በሙሉ ፈፀመ። እናም ደግሞ እኔ፣ ኔፊ፣
በጌታ እጅግ ተባረክሁ።

፱ እናም እንዲህ ሆነ የጌታ ድምፅ አባቴን
በምሽት ተናገረው፣ እናም በማግስቱ ወደ
ምድረበዳው መጓዝ እንዳለበት አዘዘው።

፲ እናም እንዲህ ሆነ አባቴ በጠዋት ተነሳ፣
እናም ወደ ድንኳኑ በር ሄደ፣ በመሬቱ ላይ
በጥበብ የተሰራውን ᵐክብ ኳስ በአድና
ቆት ተመለከተ፤ ይህም የተሰራው ከንፁህ
ነሐስ ነበር። በኳሱም ላይ ሁለት እንዝርቶች
ነበሩ፤ እናም አንደኛው በምድረበዳ ውስጥ
መሄድ ያለብንን አቅጣጫ ይጠቁማል።

፲፩ እናም እንዲህ ሆነ ወደ ምድረበዳ
መሸከም የሚያስፈልገንና ማንኛውንም ነገ
ሮች፣ እናም ጌታ የሰጠንን ቀሪ ቀለብ ሁሉ
በአንድ ላይ ሰበሰብን፤ እንዲሁም ከሁሉም
ዓይነት ዘሮች ወደ ምድረበዳው መሸከም
የምንችለውን ወሰድን።

፲፪ እናም እንዲህ ሆነ ድንኳናችንን ይዘን
የላማንን ወንዝ በማቋረጥ ወደ ምድረበዳው
ሄድን።

፲፫ እናም እንዲህ ሆነ ለአራት ቀን በስ
ተደቡብ በደቡብ-ምስራቅ አቅጣጫ ተጓ
ዝን፣ እናም እንደገና ድንኳናችንን ተከ
ልን፤ ቦታውንም ሻዘር ብለን ጠራነው።

፲፬ እናም እንዲህ ሆነ ለቤተሰቦቻችን
ምግብ የዱር እንስሳቶችን ለማደን ቀስቶቻ
ችንንና ደጋኖቻችንን ወስደን ወደ ምድረበዳ
ተጓዝን፤ ለቤተሰቦቻችንም ምግብ ካደንን
በኋላ በምድረበዳ ውስጥ በድጋሚ ወደቤ
ተሰቦቻችን ሻዘር ወደሚባለው ቦታ ተመ
ለስን። እናም በድጋሚ በምድረበዳ ውስጥ
ያንኑ አቅጣጫ በመከተል በምድረበዳው
ይበልጥ ለም በሆነው ᵐበቀይ ባህር ዳርቻ
አጠገብ ተጓዝን።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ ለብዙ ቀናት ለም
ግብ የዱር አውሬዎችን በቀስቶቻችንና፣
በደጋኖቻችንና፣ በድንጋይ እንዲሁም በወ
ንጭፋችን በመግደል ተጓዝን።

፲፮ እናም የኳሱን ᵐአቅጣጫ ተከተልን፣
እርሱም በምድረበዳ ይበልጥ ለም ወደሆ
ነው ስፍራዎች የሚመራን ነበር።

፲፯ እናም ለብዙ ቀናት ከተጓዝን በኋላ፣
እራሳችንን ለማሳረፍና ለቤተሰቦቻችንም
ምግብ ማግኘት እንድንችል ለጊዜው ድን
ኳኖቻችንን ተከልን።

፲፰ እናም እንዲህ ሆነ እኔ ኔፊ ምግብ ለማ
ደን ስሄድ፤ እነሆ፣ ከንፁህ ᵐብረት የተሰራ
ውን ደጋኔን ሰበርኩ፤ እናም ደጋኔን ከሰበ
ርኩ በኋላ፣ ምግብ ስላላገኘን እነሆ ደጋኔን
በመስበሬ ወንድሞቼ በእኔ ተናድደው ነበር።

፲፱ እናም እንዲህ ሆነ፣ ያለምንም ምግብ
ወደቤተሰቦቻችን ተመለስን፣ እናም በጉዞ
አቸው ምክንያት በጣም ደክሟቸው፣ በም
ግብ ፍላጎት ምክንያት የበለጠም ተሰቃዩ።

፳ እናም እንዲህ ሆነ፣ ላማንና ልሙኤል
እንዲሁም የእስማኤል ወንዶች ልጆች በም
ድረበዳ ውስጥ በስቃያቸውና በመከራቸው
ምክንያት እጅግ ማጉረምረም ጀመሩ፤
እናም ደግሞ አባቴ በጌታ አምላኩ ላይ
ማጉረምረም ጀመረ፤ አዎን ሁሉም እጅግ
አዝነው ነበር፤ በጌታም ላይ እንኳን አጉረ
ምርመው ነበር።

፳፩ አሁን እንዲህ ሆነ፣ እኔ ኔፊ፣ ቀስ
ቴን በማጣቴ ከወንድሞቼ ጋር ተሰቃየሁ፣
እናም ቀስታዎቻቸውም መለጠጥ ባለመቻ
ላቸው እጅግ አስቸጋሪ፣ አዎን ምግብ ማግ
ኘት እስከማይቻለን ድረስም ሆነ።

፳፪ እናም እንዲህ ሆነ፣ እኔ ኔፊ፣ እነ

ሐ ፲ ፩ ኔፊ ፲፡ ፩።
ለ ቅ.መ.መ. ጋብቻ፣ መጋባት።
ሐ ፩ ኔፊ ፱፡ ፴፭፣
፪ ኔፊ ፭፡ ፭-፮።

፲ ሀ አልማ ፴፯፡ ፴፰-፴፮።
ቅ.መ.መ. ሊያሆና።
፲፱ ሀ ት. እና ቃ. ፲፯፡ ፩።
፲፯ ሀ ፩ ኔፊ ፲፯፡ ፲፣ ፲፯፣ ፳፯፣
፲፰፣ ፲፪፣
አልማ ፴፯፡ ፴፰-፴፮።
፲፰ ሀ ፪ ሳሙ. ፳፪፡ ፴፭።

ርሱ በጌታ አምላካቸው ላይ ᐟበማጉረም ረም እንኳን ልባቸውን እንደገና በማጠጠ ራቸው ምክንያት፣ ወንድሞቼን ብዙ ተና ገርኳቸው።

፳፫ እናም እንዲህ ሆነ፣ እኔ ኔፊ፣ ከእ ንጨት ቀስት እናም ቀጥ ካለ ዱላ ደጋንን ሰራሁ፣ ስለዚህ በቀስትና ደጋን፣ በወንጭ ፍና በድንጋይ ታጠቅሁ። ᐟአባቴንም ምግብ ለማግኘት ወዴት ልሂድ? አልኩት።

፳፬ እናም እንዲህ ሆነ፣ በእኔ ቃላት ምክ ንያት እራሳቸውን ትሁት በማድረግ፣ ጌታን ᐟጠየቀ፤ እኔም ብዙ ነገሮችን በነፍሴ ኃይል ሁሉ ተናገሬአቸው ነበርና።

፳፭ እናም እንዲህ ሆነ፣ የጌታ ድምፅ ወደ አባቴ መጣ፤ እናም እርሱ በጌታ ላይ በማ ጉረምረሙ በእውነት ᐟተገሰፀ፣ ስለዚህም እጅግ ሀዘን ተሰማው።

፳፮ እናም እንዲህ ሆነ፣ የጌታ ድምፅ፣ ወደኳሱ ተመልከት፣ እናም የተፃፉትን ነገሮች አስተውል አለው።

፳፯ እናም እንዲህ ሆነ፣ አባቴ በኳሱ ላይ የተፃፉትን ነገሮች ሲያስተውል እርሱ፣ እናም ደግሞ ወንድሞቼና የእስማኤል ወን ዶች ልጆች እንዲሁም ሚስቶቻችን፣ እጅግ ፈሩና ተንቀጠቀጡ።

፳፰ እናም እንዲህ ሆነ፣ እኔ ኔፊ በኳሱ ላይ ያሉት አመልካቾች የሚሰሩት፣ ለእነ ርሱ በምንሰጣቸው ᐟእምነት፣ እናም ትጋ ትና፣ ትኩረት እንደሆነ ተመለከትኩ።

፳፱ እናም ደግሞ በእነርሱ ላይ ለማንበብ ግልፅ የነበሩ፤ የጌታን መንገድ በተመለ ከተም ᐟግንዛቤን የሚሰጡ አዲስ ፅሁፎች ተፅፎ ነበር፣ ለእርሱም በምንሰጠው እም ነትና ትጋት መሰረት ከጊዜ ወደ ጊዜ ይጻፋ ልም ይለወጣልም። በዚህም እኛ ᐟበቀላል ዘዴ ጌታ ትላልቅ ነገሮችን ለማምጣት እን ደሚችል እናያለን።

፴ እናም እንዲህ ሆነ እኔ ኔፊ በኳሱ ላይ በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት፣ ወደተራ ራው ጫፍ ሄድኩ።

፴፩ እናም እንዲህ ሆነ የዱር እንስሳትን በመግደል ለቤተሰቦቻችን ምግብ አገኘሁ።

፴፪ እናም እንዲህ ሆነ፣ ወደ ድንኳናችን የገደልኳቸውን እንስሳት ተሸክሜ ተመለ ስኩ፤ እናም አሁን እነርሱ ምግብ ማግኘቴን በተመለከቱ ጊዜ ደስታቸው ምን ያህል ነበር! እናም እንዲህ ሆነ፣ እነርሱ በጌታ ፊት እራሳቸውን ዝቅ አደረጉና ምስጋናን ለእርሱ አቀረቡ።

፴፫ እናም እንዲህ ሆነ፣ እንደገና ተጓ ዝን፣ በመጀመሪያ እንደተጓዝነው በዚ ያው አቅጣጫ አቅራቢያ ተጓዝን፤ እናም ለአጭር ጊዜ ቆይታ እናደርግ ዘንድ ለብዙ ቀናት ከተጓዝን በኋላ እንደገና ድንኳናች ንን ተከልን።

፴፬ እናም እንዲህ ሆነ ᐟእስማኤል ሞተ፤ እናም ናሆም ተብሎ በሚጠራም ቦታ ተቀ በረ።

፴፭ እናም እንዲህ ሆነ፣ የእስማኤል ሴት ልጆች አባታቸውን በማጣታቸውና በምድ ረበዳ ውስጥ ᐟበመሰቃየታቸው የተነሳ እጅግ አዘኑ፤ እናም ከኢየሩሳሌም እንዲወጡ ስላ ደረገ በአባቴ ላይ አጉረመረሙ፣ እንዲህም አሉ—አባታችን ሞቷል፤ አዎን፣ በምድ ረበዳ ውስጥ ብዙ ተንከራተትን፣ እንዲሁም በብዙ መከራ፣ ረሃብ፣ ጥማትና ድካም ተሰ ቃየን፤ ከእነዚህ ሁሉ ስቃዮች በኋላም በረ ሃብ የተነሳ በምድረበዳ ውስጥ እንጠፋለን።

፴፮ እናም እነርሱ በአባቴ ላይና ደግሞ በእኔ ላይ አጉረመረሙ፣ ወደ ኢየሩሳሌም እንደገና ለመመለስም ፈለጉ።

፴፯ እናም ላማን ለልሙኤል ደግሞም ለእስማኤል ወንዶች ልጆች እንዲህ ሲል ተናገራቸው፥ እነሆ አባታችንን፣ እናም

፳፪ ᐟ ዘፀአ. ፲፮፡ ፳፣ ዘኁል. ፲፩፡ ፩።
፳፫ ᐟ ዘፀአ. ፳፡ ፲፪፣ ሞዛያ ፲፫፡ ፳።
፳፬ ᐟ ቅ.መ.መ. ጻሎት።
፳፭ ᐟ ኤተር ፪፡ ፲፬።
ቅ.መ.መ. መገሰጽ፣ ተግሳጽ።
፳፰ ᐟ አልማ ፴፯፡ ፴።
ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
፳፱ ᐟ ቅ.መ.መ. ማስተዋል።
ለ ፪ ነገሥ. ፭፡ ፲፫፣ ያዕ. ፫፡ ፴፣
አልማ ፴፯፡ ፮–፯፣ ፻፭፣ ት. እና ቃ. ፻፳፫፡ ፲፯።
፴፩ ᐟ ፩ ኔፊ ፯፡ ፪–፮።
፴፭ ᐟ ቅ.መ.መ. ጭንቀት።

ደግሞ እራሱን በእኛ በታላላቅ ወንድሞቹ ላይ Ꮎገዢ እንዲሁም አስተማሪ ያደረገውን ወንድማችን ኔፊን Ꮎእንግደላቸው።

፴፯ አሁን ኔፊ ጌታ ከእርሱ ጋር መነጋገሩን እናም ደግሞ Ꮎመላዕክቶች እንደጎበኙትና እንዳስተማሩት ተናግሯል። ነገር ግን እነሆ እርሱ እንደዋሸን እናውቃለን፤ እነዚህንም ነገሮች የሚነገረንና፣ በብልህ ዘዴዎቹ ብዙ ነገሮችን ያደረገው፣ እኛንም እንዲያሞኘን ዘንድ፣ ምናልባትም እኛን እንግዳ ወደ ሆነው ምድረበዳ ሊመራን እንዲችል በማሰብ ነው፤ እናም በእኛ ላይ ማን ኛውንም በፍላጎቱና በሚያስደስተው መሰረት ያደርግ ዘንድ እኛን ከወሰደ በኋላ በእኛ ላይ እራሱን ንጉስና ገዢ ለማድረግ አስቦ አል። በዚህም መንገድ ወንድሜ ላማን በእ ነርሱ ልብ ቁጣን አነሳሳ።

፴፰ እናም እንዲህ ሆነ፣ ጌታ ከእኛ ጋር ነበር፤ አዎን የጌታ ድምፅ መጣ፣ ብዙ ቃላ ትም ተናገራቸው፣ እናም በብርቱ Ꮎገሰፃ ቸው፤ በጌታም ድምፅ ከተገሰፁ በኋላ ቁጣ ቸውን አቆሙና፣ ለኃጢአታቸው ንስሀ ገቡ፣ በዚህም ጌታ እንደገና ምግብ ማግ ኘት እንድንችል ባረከን፣ ስለዚህ አልጠ ፋንም።

ምዕራፍ ፲፤

ኔፊ መርከብ እንዲሰራ ታዘዘ—ወንድሞቹ ተቃወሙት—ከእስራኤል ጋር እግዚአ ብሔር ያደረገውን ታሪክ በመንገር አበ ረታታቸው—ኔፊ በእግዚእብሔር ኃይል ተሞላ—ወንድሞቹ እንዳይነኩት ተከ ለከሉ፣ አለበለዚያ ልክ እንደደረቀ ሸን በቆ ይኮማተራሉ። ከ፳፻፲፯–፳፻፲፭ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ እንደገና በምድረበዳ ውስጥ ጉዟችንን አደረግን፤ እናም ከዚያ ጊዜ በኋላ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ ተጓዝን። በምድረበዳው ውስጥም በብዙ ስቃይ ተገ ፋን፤ ሴቶቻችንም በምድረበዳ ውስጥ ልጆ ችን ወለዱ።

፪ እናም የጌታ በረከት በእኛ ላይ ታላቅ ስለነበር በምድረበዳ ውስጥ ለመኖር ስንል Ꮎጥሬ ስጋ ብንበላም ሴቶቻችን ልጆቻቸ ውን በበቂ ሁኔታ አጠቡአቸው፣ እነርሱም ጠንካራ አዎን፣ ልክ እንደወንዶችም ነበሩ፣ ካለምንም ማጉረምረም ጉዞአቸውን መታ ገስ ጀመሩ።

፫ በዚህም የእግዚአብሔር ትዕዛዛት መፈ ፀም እንዳለባቸው ተመለከትን። እናም የሰ ዎች ልጆች የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ Ꮎከጠ በቁ እርሱ ይመግባቸዋል፣ ያበረታታቸዋ ልም፣ እንዲሁም እርሱ ያዘዛቸውን ነገር መፈፀም የሚችሉበትን ዘዴ ያቀርብላቸ ዋል፤ ስለዚህ እኛ በምድረበዳ በተቀመጥን ጊዜ እርሱ የሚያስፈልጉንን ነገሮች Ꮎአቀ ረበልን።

፬ እናም እኛ ለብዙ አመታት፣ አዎን፣ ለስምንት ዓመታትም በምድረበዳ ውስጥ ተቀመጥን።

፭ እናም በበርካታ ፍራፍሬዎቹና በዱር ማሩ ምክንያት ለጋስ ብለን ወደጠራነው ምድር መጣን፤ እነዚህ ነገሮች ሁሉ በጌታ የተዘጋጁልን እንዳንጠፋ ነበሩ። እናም ባህ ርን ተመለከትን፣ ኢሬአንቱም ብለን ጠራ ነው፣ ትርጓሜውም ብዙ ውኃዎች ማለት ነው።

፮ እናም እንዲህ ሆነ በባህሩ ዳርቻ ድንኳ ኖቻችንን ተከልን፤ እናም በብዙ Ꮎመከራና ችግሮች ብንሰቃይም፣ አዎን፣ ብዙ ሆነው ሁሉንም እንኳን መፃፍ ባንችልም፣ ወደ ባህሩ ዳርቻ ስንመጣ እጅግ ደስተኞች ነበ ርን፤ እናም በብዙ ፍሬዎቹ ምክንያት ቦታ ውን ለጋስ ብለን ጠራነው።

፯ እናም እንዲህ ሆነ እኔ ኔፊ፣ በለጋሱ

፴፯ ሀ ዘፍጥ. ፴፯ ፡ ፱–፲፩፤ ፩ ኔፊ ፪ ፡ ፳፪፤ ፲፰ ፡ ፲። ለ ፩ ኔፊ ፲፯ ፡ ፴፱። ቅ.መ.መ. ግድያ። ፴፰ ሀ ፩ ኔፊ ፲ ፡ ፴–፴፩፤ ፱ ፡ ፲።

፴፱ ሀ ቅ.መ.መ. መገሰጽ፣ ተግሳጽ። ፲፤ ፪ ሀ ፩ ኔፊ ፲፯ ፡ ፲፪። ፲ ሀ ሞዛያ ፪ ፡ ፴፭፤ አልማ ፳፯ ፡ ፲፪።

ቅ.መ.መ. ታዛዥነት፣ ታዛዥ፣ መታዘዝ። ለ ፩ ኔፊ ፲ ፡ ፯። ፯ ሀ ፪ ኔፊ ፱ ፡ ፳۔

ምድር ለብዙ ቀናት ከቆየሁ በኋላ የጌታ ድምፅ ወደእኔ መጥቶ እንዲህ አለኝ—ተነስ እናም ወደ ተራራው ውጣ። እናም እንዲህ ሆነ ተነስቼ ወደ ተራራው ወጣሁ፣ እናም ወደጌታ ጮህኩ።

፳ እናም እንዲህ ሆነ ጌታ እንዲህ ሲል ተናገረኝ—ህዝብህን በዚህ ውኃ ላይ አሻግረው ዘንድ እኔ በማሳይህ ᵐቅርፅና ዘዴ መርከብ ስራ።

፳፩ እናም አልኩ—ጌታ ሆይ፣ መርከቡን አንተ ባሳየኸኝ ቅርፅና ዘዴ ለመስራት መሳሪያዎችን እሰራበት እንድችል ዘንድ የማቀልጠው የብረት አፈር ለማግኘት ወዴት ልሂድ?

፲ እናም እንዲህ ሆነ መሳሪያዎችን እሰራበት ዘንድ የብረት አፈሩን ለማግኘት ወዴት መሄድ እንዳለብኝ ጌታ ነገረኝ።

፲፩ እናም እንዲህ ሆነ እኔ ኔፊ እሳት ለማቀጣጠል ከዱር እንስሳት ቆዳ ወናፍ ሰራሁ፤ እናም እሳቱን ለማቀጣጠል የምችልበት ወናፉን ከሰራሁ በኋላ፣ እሳት አገኝ ዘንድ ሁለት ድንጋዮችን በአንድ ላይ አጋጨሁ።

፲፪ በምድረበዳ ውስጥ በምንጓዝበት ከዚህ ጊዜ በፊት ጌታ ይህንን ያህል እሳት እንድናቀጣጥል አልፈቀደም ነበር፤ እንዲህም አለ—ምግባችሁን እኔ ስለማጣፍጥላችሁ ይህን ᵐማብሰል አያስፈልጋችሁም፤

፲፫ እናም በምድረበዳ ውስጥ እኔ ብርሃን እሆናችኋለሁ፤ እናም ትዕዛዛቴን ከጠበቃችሁ መንገዱን በፊታችሁ ᵐአዘጋጅላችኋለሁ፤ ስለዚህ ትዕዛዛቴን እስከጠበቃችሁ ድረስ ወደ ᵃቃልኪዳኑ ምድር ትመራላችሁ፤ እናም የተመራችሁት በእኔ እንደ ሆነም ᵃታውቃላችሁ።

፲፬ አዎን፣ እናም ደግሞ ጌታ እንዲህ አለ—ወደ ቃልኪዳኑ ምድር ከደረሳችሁ በኋላ፣ እኔ ጌታ ᵐእግዚአብሔር መሆኔን ᵃታውቃላችሁ፤ እናም እኔ ጌታ ከጥፋት አዳንኳችሁ፤ አዎን ከኢየሩሳሌም ምድርም አወጣኋችሁ።

፲፭ ስለዚህ እኔ ኔፊ የጌታን ትዕዛዛት ለመጠበቅ ተጋሁ፣ እናም ወንድሞቼን ታማኝና ትጉ እንዲሆኑ አበረታታኋቸው።

፲፮ እናም እንዲህ ሆነ ከድንጋይ ባቀለጥኩት የብረት አፈር መሳሪያዎችን ሰራሁ።

፲፯ እናም ወንድሞቼ መርከብ ᵐለመስራት ዕቅዴን ባዩ ጊዜ በእኔ ላይ እንዲህ ብለው ማጉረምረም ጀመሩ፥ ወንድማችን ሞኝ ነው፣ መርከብ ለመስራት ያስባልና፤ አዎን እናም ደግሞ ይህንን ታላቅ ውሃዎች ማቋረጥ ይችላል ብሎ ያስባል።

፲፰ እናም ወንድሞቼ በእኔ ላይ ተማረሩ፣ እናም ለመስራት አልፈለጉም ነበር፣ ምክንያቱም እኔ መርከብ መስራት በመቻሌ እምነት አልነበራቸውም፤ እናም በጌታ ታዝዜ እንደነበርኩም አላመኑም ነበርና።

፲፱ እናም አሁን እንዲህ ሆነ እኔ ኔፊ በልባቸው ጠማርነት ምክንያት እጅግ አዝኜ ነበር፤ እናም አሁን ማዘኔን በተመለከቱ ጊዜ በልባቸው ᵐደስተኞች ነበሩ፣ እንዲህም ሲሉ በእኔ ላይ ተሳለቁ፥ መርከብ መስራት እንደማትችል እናውቃለን፣ ምክንያቱም ሚዛናዊነት እንደሌለህ እናውቃለን፤ ስለዚህ አንተ እንደዚህ ያለ ታላቅ ስራ ለማከናወን አትችልም።

፳ እና አንተ ልክ ᵐበከንቱ የልቡ ሀሳብ እንደተሳሳተ እንደ አባታችን ነህ፤ አዎን፣ እርሱ ከኢየሩሳሌም ምድር መርቶ አስወጣን፤ እናም በምድረበዳው ውስጥ ለእነዚህ በርካታ ዓመታት ተንከራተትን፤ እናም ሴቶቻችንም እርጉዝ በነበሩበት ጊዜ ለቃ፣ እናም በምድረበዳ ውስጥ ልጆችን ወለዱ፣ እናም ከሞት በስተቀር በሁሉም ነገሮች ተሰቃዩ፤ እናም በእነዚህ ነገሮች ከመሰቃየት ከኢየሩሳሌም ሳይወጡ ቢሞቱ ይሻል ነበር።

፳ ሀ ፩ ኔፊ ፲፰፡፪።
፲፪ ሀ ፩ ኔፊ ፲፯፡፪።
፲፫ ሀ አልማ ፴፯፡፴፰–፴፱።
ለ ፩ ኔፊ ፪፡፳፣
ያዕቆ. ፪፡፲፪።
ሐ ዘፀአ. ፮፡፯።
፲፩ ሀ ት.እና ቃ. ፭፡፪።
ለ ፪ ኔፊ ፩፡፬።
ቅ.መ.መ. ምስክርነት።
፲፯ ሀ ፩ ኔፊ ፲፰፡፩–፯።
፲፱ ሀ ቅ.መ.መ. ማሳደድ፣
መሳደድ።
፳ ሀ ፩ ኔፊ ፪፡፲፩።

፳፩ እነሆ በንብረታችን እና በውርስ ምድራችን ደስተኞች መሆን፣ አዎን እንዲሁም በሀሴት ልንኖር፣ በምንችልባቸው በእነዚህ በርካታ ዓመታት በሙሉ በምድረበዳ ተሰቃየን።

፳፪ እናም በኢየሩሳሌም ምድር የነበሩ ሕዝቦች ᵐፃድቅ ሕዝቦች እንደነበሩ እናውቃለን፤ ምክንያቱም እነርሱ የጌታን ህግና ውሳኔ እንዲሁም በሙሴ ህግ መሰረት ሁሉንም ትዕዛዛት ጠብቀዋልና፤ ስለዚህ እነሱ ፃድቅ ሕዝቦች እንደሆኑ አወቅን፤ እናም አባታችን ፈረደባቸው፣ እናም እኛ ቃላቱን ስለምንሰማ እንድንወጣ አደረገ፣ አዎን ወንድማችንም ልክ እንደ እርሱ ነው። እናም በእንደዚህ አይነት አነጋገር ነበር ወንድሞቼ ያጉረመረሙትና በእኛ የተማረሩት።

፳፫ እናም እንዲህ ሆነ እኔ ኔሬ እንዲህ ስል ተናገርኳቸው—የእስራኤል ልጆች የነበሩት አባቶቻችን፣ የጌታን ቃላት ባይሰሙ ኖሮ ከግብፃውያን እጅ ይወጡ ነበር ብላችሁ ታምናላችሁን?

፳፬ አዎን፣ ጌታ ሙሴን እነርሱን ከባርነት ᵐእንዲያወጣቸው ባያዘው ኖሮ ከባርነት ይወጣሉ ብላችሁ ትገምቱ ነበርን?

፳፭ አሁን የእስራኤል ልጆች ᵐበባርነት እንደነበሩ ታውቃላችሁ፤ እናም ለመጽናት አስቸጋሪ የሆኑ ስራዎችን ᶮእንደተሸከሙ ታውቃላችሁ፤ ስለዚህ ከባርነት መውጣታቸው ለእነርሱ የሚያስፈልግ ጥሩ ነገር እንደነበርም ታውቃላችሁ።

፳፮ አሁን ᵐሙሴ ያንን ታላቅ ስራ እንዲሰራ በጌታ መታዘዙን ታውቃላችሁ፤ እናም በእርሱ ᶮቃል የቀይ ባህር ውሃ ወዲህና ወዲያ ተከፍሎ እንደነበርና፣ በደረቁ መሬት እንደተጓዙ ታውቃላችሁ።

፳፯ ነገር ግን የፈርዖን ወታደሮች የሆኑት ግብፃውያን በቀይ ባህር ውስጥ እንደሰጠሙ ታውቃላችሁ።

፳፰ እናም እነርሱ በምድረበዳ ውስጥ ᵐመና እንደበሉ ደግሞ ታውቃላችሁ።

፳፱ አዎን እናም ሙሴ በእርሱ ያለውን የእግዚአብሔር ኃይል በመጠቀም ቃል እንደተናገረ፣ ድንጋዩን ᵐእንደመታና የእስራኤል ልጆች ጥማታቸውን ማርካት እንዲችሉ ውሃን እንዳወጣላቸው ታውቃላችሁ።

፴ እናም በጌታ አምላካቸው መድኃኒታቸው ቢመሩም፣ ከፊታቸው በመሄድ በቀን ቢመራቸውም፣ እናም በጨለማም ብርሃን ቢሰጣቸው፣ እናም ሰዎች እንዲቀበሉት ᵐአስፈላጊ የሆኑትን ሁሉንም መልካም ነገሮችን ቢሰራም ልባቸውን አጠጠሩበት፣ እንዲሁም አእምሮአቸውን አሳወሩ፣ እናም በሙሴ ላይ እንዲሁም በእውነተኛውና በህያው እግዚአብሔር ላይ ᶮክፉ ተናገሩ።

፴፩ እናም እንዲህ ሆነ እንደቃሉ ᵐአጠፋቸው፤ እናም እንደቃሉ ᶮመራቸው፣ እናም እንደቃሉ ሁሉንም ነገሮች ለእነርሱ አደረገ፤ እናም እንደቃሉ ያልሆነን በስተቀር የተደረገ ምንም ነገር አልነበረም።

፴፪ እናም የዮርዳኖስን ወንዝ ካቋረጡ በኋላ በምድሪቱ ያሉትን ልጆች ᵐእንዲያስወጡ፣ አዎን፣ እነርሱን እንዲያጠፉአቸውና እንዲበትኑአቸው ብርቱ አደረጋቸው።

፴፫ እናም አሁን በአባቶቻችን እንዲወጡ የተደረጉት፣ በቃልኪዳኑ ምድር ውስጥ ይኖሩ የነበሩት የዚህ ምድር ልጆች፣ ፃድ

፳፪ ሀ ፮ ኔሬ ፮፡ ፲፫።
፳፬ ሀ ዘዳ. ፫፡ ፪–፲፡
፮ ኔሬ ፲፱፡ ፲፡
፪ ኔሬ ፫፡ ፱፡ ፳፭፡ ፳።
፳፭ ሀ ዘፍጥ. ፲፭፡ ፲፫–፲፱።
ለ ዘፀአ. ፩፡ ፲፩፣ ፪፡ ፲፩።
፳፮ ሀ የሐዋ. ፯፡ ፳፪–፴፱።
ለ ዘፀአ. ፲፬፡ ፳፩–፴፩፣
፮ ኔሬ ፱፡ ፪፣
ሞዛያ ፯፡ ፲፱፣
ሔለ. ፳፡ ፲፩፣
ት. እና ቃ. ፳፡ ፫፣
ሙሴ ፩፡ ፳፭።
፳፯ ሀ ዘፀአ. ፲፮፡ ፱፡ ፲፬–፲፭፣ ፴፭፣
ዘኁል. ፲፩፡ ፯–፳፡
ዘዳግ. ፳፡ ፫፣
ሞዛያ ፯፡ ፲፱።
፳፱ ሀ ዘፀአ. ፲፯፡ ፮፣
ዘኁል. ፳፡ ፲፩፣
ዘዳግ. ፳፡ ፲፭፣
፮ ኔሬ ፳፡ ፳፩።
፴ ሀ ት. እና ቃ. ፲፳፡ ፲፳፣
፲፯፡ ፳፬–፳፭።
ለ ዘፀአ. ፴፪፡ ፳፡
ዘኁል. ፲፡ ፪–፫፣
ሕዝ. ፳፡ ፲፫–፲፮፣
ት. እና ቃ. ፲፱፡ ፳፫–፳፭።
፴፩ ሀ ዘኁል. ፳፯፡ ፳፭።
ለ ፮ ኔሬ ፭፡ ፲፭፣
ት. እና ቃ. ፶፫፡ ፲፮–፲፳።
፴፪ ሀ ዘኁል. ፴፫፡ ፶፪–፶፫፣
ኢያ. ፳፬፡ ፲።

ቃን ናቸው ብላችሁ ትገምታላችሁን? እነሆ እኔ አይደሉም እላችኋለሁ።

፴፬ እነርሱ ፃድቃን ቢሆኑ አባቶቻችን ከእነርሱ የበለጠ የተመረጡ ይሆናሉ ብላችሁ ታስባላችሁን? እኔ አይሆኑም እላችኋለሁ።

፴፭ እነሆ ጌታ ሁሉንም [ሀ]ሕዝብ በአንድ ዐይን ይመለከታል፤ [ለ]ፃድቅ የሆነ በእግዚአብሔር [ሐ]የተወደደ ነው። ነገር ግን እነሆ እነዚህ ሕዝቦች የእግዚአብሔርን ማንኛውንም ቃል አልተቀበሉም፣ እናም እነርሱ ሙሉ በሙሉ በኃጢያት ጠውልገው ነበር፤ እናም የእግዚአብሔር የቁጣው ሙላት በእነርሱ ላይ ነበር፤ እናም ጌታ ምድሪቷን በእነርሱ ላይ ረገማት፣ እንዲሁም ለአባቶቻችን ባረካት፤ አዎን፣ እነርሱ ይጠፉ ዘንድ በእነርሱ ላይ ረገማት፣ እናም አባቶቻችን በእርሷ ላይ ኃይል ይኖራቸው ዘንድ ባረከላቸው።

፴፮ እነሆ ጌታ ሰዎች [ሀ]መኖር እንዲችሉ ባት [ለ]ምድርን [ሐ]ፈጠረ፤ እናም ልጆቹ የእነርሱ ያደርጓት ዘንድ ፈጠራቸው።

፴፯ እናም ፃድቃን የሆኑትን ሀገሮች [ሀ]ያስነሳል፤ እናም ኃጢአተኞች የሚኖሩባትን ሀገር አጠፉ።

፴፰ እናም ፃድቃ[ሀ]ንን በጣም አስፈላጊ ወደሆነው ምድር መራ፤ እናም ኃጢአተኞችን [ለ]አጠፉቸው፣ እንዲሁም እነርሱ ባደረጓቸው ነገሮች ምድሪቱን ረገማት።

፴፱ በላይ በሰማይ ይገዛል፣ ምክንያቱም ሰማይ ዙፋኑ ነው፣ እናም ይህቺ ምድር [ሀ]መርገጫው ናት።

፵ እናም አምላካቸው አድርገው የሚቀበሉትን ይወዳቸዋል። እነሆ እርሱ አባቶቻችንን ወደዳቸው፣ እናም ከእነርሱ ጋር [ሀ]ቃል ኪዳን ገብቷል፣ አዎን፣ ለአብርሃም፣ [ለ]ለይስሀቅ፣ እና [ሐ]ለያዕቆብ እንኳን፤ እናም የገባቸውን ቃልኪዳኖች አስታወሰ፤ ስለዚህ እነርሱን [መ]ከግብፅ ምድር አወጣቸው።

፵፩ እናም ልክ እንደ እናንተ ልባቸውን [ሀ]ስላጠጠሩ፤ በምድረበዳ ውስጥ በበትሩ ቀጣቸው፤ እናም በክፉታቸው ምክንያት ጌታ ቀጣቸው። የሚበሩ መርዛምን [ለ]እባብ በመካከላቸው ላከ፤ እናም ከተነደፉ በኋላም [ሐ]ይድኑ ዘንድ መንገዱን አዘጋጀ፤ እናም ማድረግ ያለባቸው ነገር መመልከት ብቻ ነበር፤ እናም በድርጊቱ [መ]ቀላልነት የተነሳ ብዙዎች የጠፉ ነበሩ።

፵፪ እናም እነርሱ በተለያዩ ጊዜያት ልባቸውን አጠጠሩ፣ እናም [ሀ]በሙሴ ላይ እንዲሁም ደግሞ በእግዚአብሔር ላይ [ለ]ክፉን ተናገሩ፤ ሆኖም ወደር በሌለው በእርሱ ኃይል ወደቃልኪዳኑ ምድር እንደተመሩ እናንተ ታውቃላችሁ።

፵፫ እናም አሁን ከእነዚህ ሁሉ ነገሮች በኋላ ክፉ የሆኑበት ጊዜ መጣ፣ አዎን፣ እስኪጠወልጉም ድረስ፤ እናም እንደማስበው በዚህ ቀን ሊጠፉ የተቃረቡ ናቸው፣ ጥቂቶች በምርኮ ከሚወሰዱ በስተቀር እነርሱ የሚጠፉበት ቀን በእርግጥ እንደሚመጣ አውቃለሁ።

፵፬ ስለዚህ ጌታ አባቴን ወደ ምድረበዳው መሄድ እንዳለበት [ሀ]አዘዘው፤ እናም አይሁ

፴፭ ሀ የሐዋ. ፲፥፴፬፣ ፴፩፤
ሮሜ ፪፥፲፩፤
፪ ኔፊ ፳፮፥፳፫–፴፫።
ለ መዝ. ፶፰፥፳፪፤
፩ ኔፊ ፳፪፥፲፯።
ሐ ፩ ሳሙ. ፪፥፴፤
መዝ. ፺፯፥፲፤ ፻፵፭፥፳፤
አልማ ፲፫፥፬፤
ት. እና ቃ. ፹፪፥፲።
፴፮ ሀ ኢሳ. ፵፭፥፲፰፤
አብር. ፫፥፳፬–፳፭።
ለ ቅ.መ.መ. መፍጠር፣
ፍጥረት።
ሐ ቅ.መ.መ. ምድር።
፴፯ ሀ ምሳ. ፲፬፥፴፬፤
፩ ኔፊ ፬፥፲፫፤
ኤተር ፪፥፲፤
ት. እና ቃ. ፻፲፯፥፮።
፴፰ ሀ ቅ.መ.መ. የቃል ኪዳን
ምድር።
ለ ዘሌዋ. ፳፥፳፪።
፴፱ ሀ ኢሳ. ፷፮፥፩፤
ት. እና ቃ. ፴፰፥፲፯፤
አብር. ፪፥፯።
፵ ሀ ቅ.መ.መ. የአብርሐም ቃል
ኪዳን።
ለ ዘፍጥ. ፳፩፥፲፪፤
ት. እና ቃ. ፳፯፥፲።
ሐ ዘፍጥ. ፳፰፥፩–፭።
መ ዘዳግ. ፬፥፴፯።
፵፩ ሀ ፪ ነገሥ. ፲፯፥፯–፳፫።
ለ ዘኁል. ፳፩፥፬–፱፤
ዘዳግ. ፰፥፲፭፤
አልማ ፴፫፥፲፰–፳፪።
ሐ ዮሐ. ፫፥፲፫–፲፭፤
፪ ኔፊ ፳፭፥፳።
መ አልማ ፴፯፥፵፬–፵፯፤
ሔለ. ፰፥፲፭።
፵፪ ሀ ት. እና ቃ. ፹፬፥፳፫–፳፬።
ለ ዘኁል. ፲፬፥፩–፲፪።
ቅ.መ.መ. አመጽ።
፵፬ ሀ ፩ ኔፊ ፪፥፩–፪።

ዶች ሊገድሉት ሞከሩ፤ አዎን ^እናንተም ደግሞ ልትገድሉት ሞከራችሁ፤ ስለዚህ እናንተ ህይወቱን ለማጥፋት ፈለጋችሁ፣ ስለሆነም እናንተ በልባችሁ ገዳዮች ናችሁ፣ እናም ልክ እንደ እነርሱ ናችሁ።

፡፳፩ እናንተ ክፉን ለማድረግ ^ፈጣን፣ ግን ጌታ አምላካችሁን ለማስታወስ የምትዘገዩ ናችሁ። ^መልአክን አይታችኋል፣ እናም ተናግሯችኋል፤ አዎን ድምፁንም በየጊዜው ሰምታችኋል፤ እናም በትንሽ ለስላሳ ድምፅ ተናግሯችኋል፣ ነገር ግን እናንተ ^ደንዝዛ ችኋል፣ ስለዚህ ቃሉ ሊሰማችሁ አልቻ ለም፤ ስለዚህ እርሱ ሲናገራችሁ ድምፁ ልክ መሬትን እንደምትሰነጠቅ አይነት እን ድትናወጥ እንዳደረጋት ነጎድጓድ ነበር።

፡፳፪ እናም ደግሞ ጌታ ^ኃያል በሆነው ቃሉ ኃይል መሬት ከእንግዲህ ወዲህ እንዳትኖር ማድረግ እንደሚችል ታውቃላችሁ፤ አዎን እናም በቃሉ ጠማማውን ማቃናት እንደሚ ችል ታውቃላችሁ፣ እናም የተቃናው ቦታ ይሰበራል። አቤቱ፣ ለምን እናንተ በልባ ችሁ ደንዳኖች ትሆናላችሁ?

፡፳፫ እነሆ በእናንተ ምክንያት ነፍሴ ተጨነቀች፣ እንዲሁም ልቤ ቆስሏል፤ ለዘለዓለም እናንተ እንዳትጣሉ እፈራለሁ። እነሆ በእግዚአብሔር መንፈስ ^በመሞላቴ ሰውነቴም ^ጥንካሬ የለውም።

፡፳፬ እናም አሁን እንዲህ ሆነ እነዚህን ቃላት ስናገር እነርሱ በእኔ ተቆጥተው ነበር፣ እና ወደባህር ጥልቅ ሊወረውሩኝ ፈለጉ፤ እናም ሊይዙኝ ወደእኔ ሲመጡ እንዲህ በማለት ተናገርኳቸው—ሁሉን በሚገዛው በእግዚአብሔር ስም ^እንዳትነኩኝ አዛች ኋለሁ፣ ስጋዬ እስከሚበላ ድረስ በእግዚአ ብሔር ^ኃይል ተሞልቻለሁና፤ እና ማን ኛውም እጁን በላዬ ላይ ያደረገ እንደደረቀ ሸንበቆ ^ይኮማተራል፣ እንዲሁም በእግዚ አብሔር ኃይል ፊት እንደከንቱ ነገር ይሆ ናል፣ እግዚአብሔር ይቀጣዋልና።

፡፳፭ እናም እንዲህ ሆነ እኔ ኔፊ፣ በአባ ታቸው ላይ ከእንግዲህ ማጉረምረም እን ደሌለባቸው፣ ከእኔ ጋር ለመስራት መቃ ወም እንደሌለባቸው ተናገርኳቸው፤ ምክ ንያቱም እግዚአብሔር መርከብ እንድሰራ አዞኛልና።

፡፳ እናም እንዲህ አልኳቸው—እግዚአብ ሔር ሁሉንም ነገሮች እንድሰራ ^ካዘዘኝ፣ መስራት እችላለሁ። እርሱ ይህንን ውሃ ወደ ምድር ተለወጥ እንድለው ካዘዘኝ ውሃውም ምድር ይሆናል፤ እናም ይህንንም ካልኩት እንዳዘዝኩት ይሆናል።

፡፳፩ እናም አሁን ጌታ ይህን ያህል ታላቅ ኃይል ካለው፣ እንዲሁም በሰዎች ልጆች መካከል ብዙ ተዓምራትን ካደረገ፣ እኔም መርከቡን መስራት እንድችል ^ማስተማር እንዴት አይቻለውም?

፡፳፪ እናም እንዲህ ሆነ እኔ ኔፊ ለወንድ ሞቼ ብዙ ነገሮችን ስለተናገርኳቸው ዝም አሉ፣ እናም ከእኔ ጋር መከራከር አልቻ ሉም፤ ለብዙ ቀናትም እጃቸውን በእኔ ላይ መጫንም ሆነ በጣቶቻቸው ሊነኩኝ አል ደፈሩም። አሁን፣ የእግዚአብሔር ^መን ፈስ እጅግ ኃይለኛ ስለነበረ፣ ይህን ለማ ድረግ ያልደፈሩትም፣ በእኔ ፊት እንዳይ ኮማተሩ ፈርተው ነው፤ እናም እንደዚህም በእነርሱ ላይ ተፅዕኖ ነበረው።

፡፳፫ እናም እንዲህ ሆነ፣ ጌታ እንዲህ አለኝ—በወንድሞችህ ላይ እንደገና እጅ ህን ዘርጋ እናም እነርሱ በአንተ ፊት አይ ኮማተሩም፣ ነገር ግን አንቀጠቅጣቸዋለሁ፣ እናም ይህንን የማደርገው አለ ጌታ፣ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ያውቁ ዘንድ ነው።

፡፳፬ እናም እንዲህ ሆነ፣ በወንድሞቼ ላይ እጄን ዘረጋሁ፣ እናም እነርሱ አልተ

ሚ፲፩ ለ ፩ ኔፊ ፲፮፡ ፡ሚ፲፯።
ሚ፲፭ ሀ ሞዛያ ፲፫፡ ፡፳፱።
ለ ፩ ኔፊ ፡፡፡ ፡፫።
ሐ ኤፌ. ፡፡፡ ፡፲፱።
ሚ፲፮ ሀ ሔስ. ፲፪፡ ፲–፲፰።
ሚ፲፯ ሀ ሚክ. ፫፡ ፡፰።
ለ ፩ ኔፊ ፲፱፡ ፡፳።
ሚ፲፰ ሀ ሞዛያ ፲፫፡ ፡፫።
ለ ፪ ኔፊ ፩፡ ፡፳፯–፡፳፯።
ቅ.መ.መ. ሀይል።
ሐ ፩ ነገሥ. ፲፫፡ ፡፡–፲።
፪ ሀ ፊልጵ. ፡፡፡ ፲፫፣
፩ ኔፊ ፫፡ ፲።
ሚ፲፩ ሀ ዘፍጥ. ፲፡ ፲፡–፲፯፣
፩ ኔፊ ፲፣ ፡፩።
ሚ፲፪ ሀ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።

ኮማተሩም ነበር፤ ነገር ግን ጌታ ልክ እን ደተናገረው አንቀጠቀጣቸው።

፶፭ እናም ከዚያ ጌታ ከአንተ ጋር መሆ ኑን በእርግጥ እናውቃለን፣ የጌታ ኃይልም እኛን እንዳንቀጠቀጠን እናውቃለንና አሉ። እናም በፊቴ ወደቁ፣ እና እኔን ᵐለማምለክ ሞክሩ፣ ነገር ግን እኔን እንዲያመልኩ አል ፈቀድኩላቸውም፣ እንዲህም አልኩ—እኔ ወንድማችሁ ነኝ፣ አዎን፣ ታናሽ ወንድማ ችሁ፤ ስለዚህ ጌታ አምላካችሁን አምልኩ፣ እናም አባትና እናታችሁን አክብሩ፣ ጌታ አምላካችሁ በሚሰጣችሁ ምድር ᵃእድሜ ያችሁ እንዲረዝም።

ምዕራፍ ፲፰

መርከቡ ተጠናቀቀ—የያዕቆብና የዮሴፍ መወለድ ተጠቀሰ—ህዝቡም ወደ ቃል ኪዳኑ ምድር ተጓዙ—የእስማኤል ወን ዶች ልጆችና ሚስቶቻቸው በፈንጠዚያ ውና በአመፃው ተቀላቀሉ—ኔፊ ታሰረ፣ እናም መርከቡ በኃይለኛ አውሎ ነፋስ ወደኋላ ተነዳች—ኔፊ ተፈታ፣ እናም በእርሱ ፀሎት ማዕበሉ ቆመ—ህዝቡም ወደ ቃልኪዳኑ ምድር ደረሱ። ከ፳፻፲፭–፳፻፲፱ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ እነርሱ ጌታን አመለ ኩና ከእኔ ጋር ሄዱ፤ እና ልዩ አይነት አሰ ራር ባለው እንጨት ስራ ሰራን። ጌታም የመርከቡን እንጨቶች እንዴት መስራት እንዳለብኝ በየጊዜው ያሳየኝ ነበር።

፪ አሁን እኔ ኔፊ ይህንን እንጨት የቀረ ፅኩት ከሰው በተማርኩት መልኩ አልነበ ረም፣ መርከቡንም ቢሆን የሰራሁት በሰ ዎች መንገድ አልነበረም፤ ነገር ግን ጌታ ለእኔ ባሳየኝ መንገድ ነበር የሰራሁት፤ ስለ ዚህ ይህም በሰዎች መንገድ የተመሰረተ አልነበረም።

፫ እና እኔ ኔፊ ወደተራራው ሁልጊዜ እሄድ ነበር፣ እና እኔ ሁልጊዜ ወደጌታ ᵐእፀልይ ነበር፤ ስለዚህ ጌታ ለእኔ ታላቅ ነገሮችን ᵃአሳየኝ።

፬ እናም እንዲህ ሆነ የጌታን መመሪያ በመከተል መርከቡን ከጨረስኩ በኋላ ወን ድሞቼ ጥሩ እንደሆነና አሰራሩም እጅግ ረቂቅ እንደሆነ ተመለከቱ፤ ስለዚህ እን ደገና ራሳቸውን በጌታ ᵐፊት ዝቅ አደረጉ።

፭ እናም እንዲህ ሆነ፣ ተነስተን ወደ መር ከቡ እንድንወርድ፣ የጌታ ድምፅ ወደአ ባቴ መጣ።

፮ እናም እንዲህ ሆነ በማግስቱ ከምድ ረበዳ ብዙ ፍሬዎችን፣ ᵐስጋን፣ በቂ ማር፣ ጌታ እንደአዘዘን ስንቅና ሁሉን ነገሮች ካዘ ጋጀን በኋላ ከሁሉም ጭነታችንና ዘሮቻ ችን እናም ከእኛ ጋር ያመጣናቸውን ነገ ሮች በሙሉ ይዘን፣ እያንዳንዱ እንደ እድ ሜው ወደመርከቡ ወረድን፣ ስለዚህ ሁላች ንም ከሚስቶቻችንና ከልጆቻችን ጋር ወደ መርከቡ ወረድን።

፯ እና አሁን አባቴ ሁለት ልጆች በምድ ረበዳ ወልዷል፤ ታላቁ ᵐያዕቆብ፣ ታናሹ ᵃዮሴፍ ይባሉ ነበር።

፰ እናም እንዲህ ሆነ ሁላችንም የታዘዝ ነውን ከያዝንና ስንቃችንን ይዘን ወደመር ከቡ ውስጥ ከወረድን በኋላ ᵐበባህሩ ጉዞን ጀመርን፣ እናም በነፋሱ ፊት ወደ ᵃቃል ኪዳኑ ምድር ተገፋን።

፱ እናም ለብዙ ቀናት በነፋሱ ከተመ ራን በኋላ፣ እነሆ ወንድሞቼ እና የእስማ ኤል ልጆች እናም ሚስቶቻቸው መደሰት፣ መጨፈርና መዝፈን እንዲሁም ብዙ መጥፎ ነገር መናገር ጀመሩ፣ አዎን፣ በምን ኃይል ወደዚያ ቦታ እንደመጡ እንኳን ረሱት፤ አዎን ክፋታቸውም እጅግ ታላቅ ሆነ።

፲ እናም እኔ ኔፊ በኃጢኣታችን ምክንያት ጌታ እንዳይቆጣንና እንዳይቀጣን በባህርም

፶፭ ሀ የሐዋ. ፲፡፡ ፲፩–፲፭።
ለ ዘፀእ. ፳፡፲፪፣ ሞዛያ ፲፫፡፳።
፲፰ ፲ ሀ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
ለ ቅ.መ.መ. ራዕይ።
፩ ሀ ፩ ኔፊ ፲፯፡፭።
፪ ሀ ፩ ኔፊ ፲፯፡፪።
፯ ሀ ፪ ኔፊ ፪፡፩።
ለ ፪ ኔፊ ፲፡፩።
፰ ሀ ፪ ኔፊ ፲፡፳።
ለ ፩ ኔፊ ፪፡፳።
ቅ.መ.መ. የቃል ኪዳን ምድር።

ጥልቅ ውስጥ እንዳንሰምጥ እጅግ መፍራት ጀመርኩ፤ ስለዚህ እኔ ነፊ በጥሞና እናገራ ቸው ጀመርኩ፤ ነገር ግን እነሆ እነርሱ በእኔ [ሀ]ተቆጡ፣ እንዲህም አሉ—ታናሽ ወንድ ማችን በእኛ ላይ [ለ]መሪ እንዲሆን አንፈቅ ድም።

፲፩ እናም እንዲህ ሆነ ላማንና ልሙኤል ወስደው በገመድ አሰሩኝ፣ በጣም አጎሳ ቆሉኝ፤ ይሁን እንጂ ስለጋጥአን የተናገረው ቃል በሙሉ ይፈፀም ዘንድ ጋይሉን ሊያ ሳይ ስለፈለገ ጌታ ይህን [ሐ]ፈቀደ።

፲፪ እናም እንዲህ ሆነ መነቃነቅ እስኪ ያቅተኝ ካሰሩኝ በኋላ በጌታ የተዘጋጀው [ሀ]አቅጣጫ ጠቋሚ መስራቱን አቆመ።

፲፫ ስለዚህ መርከቧንም ወዴት መምራት እንዳለባቸው አላወቁም፣ በዚህም ምክን ያት ታላቅ ማዕበል አዎን ታላቅና አስፈሪ አውሎ ንፋስ ተነሳ፣ እናም ለሶስት ቀናት ያህል ወደ ኋላ [ሀ]ተነዳን፣ እናም በባህር ውስጥ እንዳይሰምጡ መፍራት ጀመሩ፤ ይሁን እንጂ እኔን አልፈቱኝም።

፲፬ እናም ወደ ኋላ ስንነዳ በነበርንበት በአ ራተኛው ቀን ማዕበሉ እጅግ በረታ።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ ወደ ባህሩ ጥልቅ ልንሰጥም ነበር። እናም ለአራት ቀን በባህሩ ላይ ወደ ኋላ ከተነዳን በኋላ ወንድሞቼ የጌታ ፍርድ በእነርሱ ላይ መሆኑንና ከኃጢአታ ቸው ንስሀ ካልገቡ በስተቀር እንደሚጠፉ [ሀ]መገንዘብ ጀመሩ፤ ስለዚህ ወደ እኔ መጡና የታሰርኩበትን ከክንዶቼ ላይ ፈቱ፣ እነር ሱም አብጠው ነበር፤ እናም ደግሞ ቁር ጭምጭሚቶቼም እጅግ አብጠው ነበር፣ ሁለቱም እጅግ ቆስለው ነበር።

፲፮ ይሁን እንጂ ወደ አምላኬ ተመለከ ትኩ፣ እናም ቀኑን ሙሉ እርሱን [ሀ]አመሰ ገንኩ፤ እናም በመከራዬ የተነሳ በጌታ ላይ አላጉረመረምኩም።

፲፯ አሁን አባቴ ሌሂ እነርሱን እናም ደግሞ [ሀ]የእስማኤልን ወንድ ልጆች ብዙ ነገ ሮች ተናገሯቸው ነበር፤ ነገር ግን እነሆ ስለ እኔ የሚናገርን ማንንም ሰው በብዙ ማስፈ ራሪያ ተናግረው ነበር፤ እና ወላጆቼ በእር ጅና በመያዝና በልጆቻቸው ምክንያት በሀ ዘን በብርቱ ስለተሰቃዩ ደካማ ሆኑ፣ አዎን አልጋቸው ላይም በበሽታ ወደቁ።

፲፰ በሀዘናቸው ብዛትና በወንድሞቼ ኃጢ ያት የተነሳ ከዚህ ህይወት ወደሚወሰዱበ ትና አምላካቸውን ወደሚገናኙበት ደርሰው ነበር፣ አዎን ያረጀ ሰውነታቸውም በአፈር ውስጥ ሊወድቁ እየደረሱ ነበሩ፤ አዎን በሀ ዘን ወደ ውኃማው መቃብር የሚጣሉበት ጊዜ እየቀረበ ነበር።

፲፱ እናም ያዕቆብና ዮሴፍ ልጆች እንደ መሆናቸው ብዙ እንክብካቤ ይፈልጉ ስለ ነበር፣ በእናታቸው ስቃይ ምክንያት አዝ ነው ነበር፤ ደግሞም [ሀ]የባለቤቴና የልጆቼ እንባና ፀሎት ይፈቱኝ ዘንድ የወንድሞቼን ልብ አላራራም።

፳ እና በጥፋት ካስፈራራቸው የእግዚአ ብሔር ኃይል በስተቀር ልባቸውን የሚ ያራራ ምንም ነገር አልነበረም፤ ስለዚህ በባህሩ ጥልቅ ሊዋጡ እንደሆነ ባዩ ጊዜ ለሰሩት ስራ ንስሀ ገቡ፣ በዚህም ምክንያት እኔን ፈቱኝ።

፳፩ እናም እንዲህ ሆነ እኔን ከፈቱኝ በኋላ አቅጣጫ ጠቋሚውን ወሰድኩት፣ እንደፈ ለኩትም ሰራ። እናም እንዲህ ሆነ እኔ ለጌታ ፀለይኩ፤ ከፀለይኩም በኋላ ነፋሱም፣ ማዕ በሉም ቆመ፣ ታላቅ ፀጥታም ሆነ።

፳፪ እናም እንዲህ ሆነ እኔ ነፊ መርከቡን መራሁ፣ እንደገናም ወደቃልኪዳኑ ምድር ተጓዝን።

፳፫ እናም እንዲህ ሆነ ለብዙ ቀናት ከተ ጓዝን በኋላ፣ [ሀ]በቃልኪዳኑ ምድር ደረስን፤

፲ ሀ ፩ ነፊ ፲፯፡፲፯–፻፳።
ለ ዘፍጥ. ፴፯፡፱–፲፩፤ ፩ ነፊ ፲፯፡፴፣፴፤ ፪ ነፊ ፩፡፳፳–፳፭።
፲፩ ሀ አልማ ፲፡፲፩።
፲፪ ሀ ፩ ነፊ ፲፯፡፲፣ ፲፯፣ ፳፯፤ ፪ ነፊ ፭፡፲፪፤ አልማ ፴፯፡፴፣፴፤ ት. እና ቃ. ፲፯፡፩።
፲፫ ሀ ሞዛያ ፩፡፲፯።
፲፭ ሀ ሔለ. ፲፪፡፫።
፲፯ ሀ አልማ ፴፯፡፳፳።
፲፰ ሀ ፩ ነፊ ፯፡፱–፳።
፲፱ ሀ ፩ ነፊ ፯፡፲፱፣ ፲፯፡፯።
፳፫ ሀ ቅ.መ.መ. የቃል ኪዳን ምድር።

እናም በምድሩ ላይ ሄድንና፣ ድንኳኖቻ ችንን ተከልን፤ የቃልኪዳኑ ምድር ብለ ንም ጠራነው።

፳፬ እናም እንዲህ ሆነ መሬቱን ማረስ ጀመርን፣ ዘሮችንም መዝራት ጀመርን፤ አዎን ከኢየሩሳሌም ያመጣናቸውን ዘሮች በሙሉ ዘራናቸው። እናም እንዲህ ሆነ ዘሮቹ እጅግ አደጉ፤ ስለዚህ በብዙ ተባረክን።

፳፭ እናም እንዲህ ሆነ በቃል ኪዳን ምድር ውስጥ በምድረበዳው በተጓዝን ጊዜ ሁሉም አይነት እንስሳት ላም፣ በሬ፣ እና አህያና ፈረስ፣ እናም ፍየልና የዱር ፍየል፣ እን ዲሁም ሁሉም አይነት ለሰው ጥቅም የሚ ውሉ የዱር እንስሳት በጫካው ውስጥ እን ደነበሩ አገኘን። እንዲሁም ሁሉም አይነት የወርቅ፣ የብርና፣ የመዳብ የብረት አፈር አገኘን።

ምዕራፍ ፲፱

ነፊ ሰሌዳዎችን ከብረት አፈር ሠርቶ የህ ዝቡን ታሪክ መዘገበ—የእስራኤል አም ላክ ሌሂ ኢየሩሳሌምን ከለቀቀበት ከስድ ስት መቶ ዓመት በኋላ ይመጣል—ስለእ ርሱ መከራና ስቅለት ነፊ ተናገረ—አይሁ ዶች ይጠላሉ፣ እናም ወደጌታ እስከሚመ ለሱ እስከ ኋለኞቹ ቀናት ድረስ ይበተናሉ። ከ፭፻፹፯–፭፻፸ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ ጌታ አዘዘኝ፣ ስለዚህ የህዝቤን ታሪክ እፅፍባቸው ዘንድ ᵐሰሌዳዎ ችን ከብረት አፈር ሰራሁ። እናም በሰሌዳ ዎቹ ላይ ᵃየአባቴን ታሪክ፣ ደግሞም የምድ ረበዳ ጉዞአችንንና የአባቴን ትንቢቶች ፃፍ ኩባቸው፤ ደግሞም ብዙዎቹን የእኔን ትን ቢቶች ፃፍኩባቸው።

፪ እናም እነርሱንም በሰራሁ ጊዜ ᵐእነ ዚህን ሰሌዳዎች እንድሰራ ከጌታ እንደ ምታዘዝ አላወቅሁም ነበር፤ ስለዚህ የአባ ቴን ታሪክና የአባቶቹን የትውልድ ሐረግ፣ እናም በምድረበዳ የነበሩትን አብዛኞች ገጠ መኞቻችን የተፃፉት በእነዚያ እኔ ባልኳ ቸው የመጀመሪያ ሰሌዳዎች ላይ ነው፤ ስለዚህ እኔ ᵃእነዚህን ሰሌዳዎች ከመስራቴ በፊት የተከሰቱት ነገሮች በይበልጥም በመ ጀመሪያዎቹ ሰሌዳዎች በእውነትም ተጠ ቅሰዋል።

፫ እናም እነዚህን ሰሌዳዎች በትዕዛዝ ከሰ ራሁ በኋላ፣ እኔ ነፊ፣ አገልግሎትና ትንቢ ቶችን ግልፅና አስፈላጊ የሆኑትን ክፍሎች፣ ᵐበእነዚህ ሰሌዳዎች ላይ እንድፅፍ ትዕዛዝ ተቀበልኩ፤ እና የሚፃፉት ነገሮች ይህችን ምድር ለሚይዙት ህዝቦቼ መመሪያ ይሆኑ ዘንድ፣ ደግሞም እኔ ለማላውቀው፣ ጌታ ለሚያውቀው፣ ᵃለመልካም ዓላማው ይሆኑ ዘንድ ይጠበቃሉ።

፬ ስለዚህ እኔ ነፊ፣ በሌሎች ሰሌዳዎች ላይ የህዝቦቼን ጦርነት፣ ፀብ፣ እና ጥፋትን ታሪክ፣ ወይም የተዘረዘረ ታሪክ መዘገብኩ። እናም ይህን አደረኩ፣ ህዝቤንም እኔ ስሄድ ምን ማድረግ እንዳለባቸውና፣ ከጌታ ተጨ ማሪ ትዕዛዝ እስከሚመጣ ድረስ፣ እነዚህ ሰሌዳዎች ከአንዱ ትውልድ ወደሌላው ወይም ከአንዱ ነቢይ ወደሌላው መተላለፍ እንደሚገባቸው አዘዝኩኝ።

፭ እነዚህን ሰሌዳዎች እንዴት ᵐእንደሰ ራሁ ከዚህ በኋላ ይነገራል፣ እናም እነሆ እንደተናገርኩት እቀጥላለሁ፤ ይህንንም የማደርገው እጅግ የተቀደሱትን ነገሮች ህዝቦቼ ያውቁት ዘንድ ᵃእንዲጠብቁ ነው።

እርሱን እንደ ᐪንጉስ ወይም ተከላካይ በም ታምኑትና፣ በእርሱ ለጥበቃችሁ ተስፋ በምታደርጉ በወንድሜ ኔፊ የተቀባሁት እኔ ያዕቆብ፣ እነሆ፣ እኔ እጅግ ብዙ ነገሮችን እንደተናገርኳችሁ ታውቃላችሁ።

፲ ሆኖም እኔ እንደገና እናገራችኋለሁ፤ ምክንያቱም ለነፍሳችሁ ደህንነት ፍላጎት አለኝና። አዎን፣ ለእናንተ ጭንቀቴ ታላቅ ነው፤ እናም እናንተ ሁልጊዜ ይህ እንደ ሚሆን ታውቃላችሁ። እኔ በሙሉ ትጋት መክሬአችኋለሁ፤ እናም የአባቴን ቃል አስ ተምሬአችኋሁ፤ እናም ከዓለም መፈጠር ጀምሮ ሁሉንም የተፃፉ ነገሮች በተመለ ከተ አነጋግሬአችኋለሁ።

፲፩ እናም አሁን፣ እነሆ፣ ስላሉትና ስለሚ መጡት ነገሮች እነግራችኋለሁ፤ ስለዚህ፣ ᐪየኢሳይያስን ቃል አነብላችኋለሁ። እናም እነርሱ ወንድሜ ለእናንተ እንድናገር የፈለ ጋቸው ቃላት ናቸው። እናም የምናገራችሁ ለእናንተ ጥቅም፣ እናንተ አምላካችሁን ታውቁትና ስሙንም ታወድሱ ዘንድ ነው።

፲፪ እናም አሁን እኔ የማነባቸው ቃላት ኢሳይያስ የእስራኤልን ቤት በተመለከተ የተናገራቸው ናቸው፤ ስለሆነም፣ ከእናን ተም ጋር ተመሳሳይነት አላቸው፣ ምክን ያቱም እናንተ ከእስራኤል ቤት ናችሁና። እናም ከእስራኤል ቤት ስለሆናችሁ በኢሳ ይያስ የተነገሩ ለእናንተ የሚተገበሩ ብዙ ነገሮች አሉ።

፲፫ እናም አሁን፣ ቃላቱ እነዚህ ናቸው፥ ጌታ እግዚአብሔር ᐪእንዲህ ይላል—እነሆ እጄን ወደ አህዛብ አነሳለሁ፣ ᐪአርማዬንም ወደ ወገኖች አቆማለሁ፤ ወንዶች ልጆችሽ ንም በክንዳቸው ያመጡአቸዋል፥ ሴቶች ልጆችሽንም በጫንቃቸው ይሸከሟቸዋል።

፲፬ ነገሥታትም አሳዳጊ አባቶችሽ ይሆ ናሉ፣ እቴጌዎቻቸውም ሞግዚቶችሽ ይሆ ናሉ፤ ፊታቸውን ወደ ምድር ዝቅ አድር ገው ይሰግዱልሻል፣ የእግራችሁንም ትቢያ ይልሳሉ፤ እናም እኔ ጌታ መሆኔን ታውቂያ ለሽ፤ እኔን ᐪየጠበቁ አያፍሩምና።

፲፭ እናም አሁን እኔ ያዕቆብ እነዚህን ቃላት በተመለከተ በመጠኑ እናገራለሁ። እነሆም ጌታ እኛ ከመጣንበት ᐪበኢየሩሳሌም የነበ ሩት እንደተገደሉና በምርኮ ᐪእንደተወሰዱ አሳይቶኛል።

፲፮ ሆኖም፣ ጌታ እነርሱ እንደገና ᐪእንደ ሚመለሱ አሳይቶኛል። እናም ደግሞ ጌታ እግዚአብሔር፣ የእስራኤሉ ቅዱስ፣ በስጋ እራሱን እንደሚገልፅላቸው፤ እናም መል አኩ ለእኔ በተናገረው ቃል መሠረት፣ እራ ሱን ከገለፀ በኋላ ይገርፉታልም ᐪይሰቅሉ ታልም።

፲፯ እናም በእስራኤሉ ቅዱስ ላይ ልባቸውን ካጠጠሩና አንገታቸውን ካደነደኑ በኋላ፣ እነሆ፣ የእስራኤል ቅዱስ ᐪፍርድ በእነርሱ ላይ ይመጣል። እናም እነርሱ የሚቀጡበ ትና የሚሰቃዩበት ቀን ይመጣል።

፲፰ ስለሆነም፣ መላኩ እንዳለው፣ ወዲ ህና ወዲያ እንዲዘዋወሩ ከተደረጉ በኋላ፣ ብዙዎቹ በስጋ ይሰቃያሉ፣ በታማኝ ፀሎ ቶች የተነሳም እንዲጠፉ አይደረጉም፤ እነ ርሱ ይበተናሉ፣ ይገረፋሉ፣ እናም ይጠ ላሉ፤ ይሁን እንጂ፣ ጌታ ለእነርሱ መሀሪ ይሆናል፣ መድኃኒታቸውንም ᐪሲያውቁት ወደ ርስት ምድራቸው በድጋሚ በአንድ ላይ ᐪይሰበሰባሉ።

፲፱ እናም ነቢያት የፃፉላቸው ᐪአህዛብ የተባረኩ ናቸው፤ እነሆም፣ እነርሱ ንስሀ ከገቡና ከፅዮን ካልተዋጉ፣ እና እራሳቸ

፲፯ ፪ *ሀ* ያዕቆ. ፩፡፱፣ ፲፩።
፱ *ሀ* ፫ ኔፊ ፳፫፡፩።
፲፯ *ሀ* ኢሳ. ፵፱፡፳፪–፳፫።
ለ ቅ.መ.መ. ምልክት።
፲፰ *ሀ* ት.እና ቃ. ፻፴፫፡፵፭፣ ሙሴ ፩፡፲፯።
፲፱ *ሀ* አስቴ. ፪፡፲፣ ፩ ኔፊ ፲፡፣ ፩ ኔፊ ፳፡፲፣ ፪ ኔፊ ፳፭፡፲፣ ኦምኒ ፩፡፲፭፣ ሔለ. ፲፡፳–፳፩።
ለ ፪ ነገሥ. ፳፡፱፣ ፲–፲፯፣ ፳፭፡፩–፲፪። ቅ.መ.መ. እስራኤል—የተበተኑት እስራኤል።
፲፱ *ሀ* ፩ ኔፊ ፲፡፫።
ለ ፩ ኔፊ ፲፱፡፲፣ ፲፣ ፲፫፣ ሞዛያ ፫፡፱፣ ፫ ኔፊ ፲፩፡፲፩–፲፭። ቅ.መ.መ. መሰቀል።
፲ *ሀ* ማቴ. ፳፯፡፳፡–፳፭።
፲፩ *ሀ* ሆሴ. ፫፡፭፣ ፩ ኔፊ ፳፪፡፲፩፣ ፪ ኔፊ ፱፡፪። *ለ* ቅ.መ.መ. እስራኤል—የእስራኤል መሰብሰብ።
፲፪ *ሀ* ፩ ኔፊ ፲፡፡–፩፣ ፪ ኔፊ ፲፡፱–፲።

ውን ከታላቋና ^የርኩሰት ቤተክርስቲያን አንድ ካላደረጉ ይድናሉ፤ ጌታ እግዚአብሔር ለልጆቹ የገባውን ሐቃል ኪዳን ይፈፅማልና፤ እናም ለዚህ ነው ነቢዩ እነዚህን ነገሮች የፃፈው።

፲፫ ስለዚህ፣ ከፅዮን ጋርና ከጌታ የቃል ኪዳን ህዝብ ጋር የሚዋጉ የእግሮቻቸውን ትቢያ ይልሳሉ፤ እናም የጌታ ህዝቦች ᵛአያፍሩም። የጌታ ህዝቦች እርሱን ^የሚጠብቁ ናቸውና፤ አሁንም የመሲሁን መምጣት ይጠብቃሉና።

፲፬ እናም እነሆ፣ በነቢዩ ቃላት መሠረት መሲሁ ᵛለሁለተኛ ጊዜ እነርሱን ለማደስ እንደገና ይጀምራል፤ ስለዚህ፣ በእርሱ የሚያምኑበት ያ ቀን ሲመጣ፣ እራሱን በኃይልና በታላቅ ክብር ጠላታቸውን ^በመደምሰስ ሐይገልፃል፤ እናም በእርሱ የሚያምኑትን አንዳቸውንም አያጠፉም።

፲፭ እናም በእርሱ የማያምኑ ᵛበእሳትና፣ በአውሎ ነፋስ፣ በመሬት መንቀጥቀጥና፣ በደም መፍሰስ፣ ^በቸነፈር፣ በረሀብና፣ በድርቅ ሐይጠፋሉ። እናም ጌታ እግዚአብሔር የእስራኤል ቅዱስ መሆኑን ያውቃሉ።

፲፮ ᵛአደን ከሃያሉ ይወሰዳልን፣ ወይስ ^የህጋዊ ምርኮኞች ያመልጣሉን?

፲፯ ነገር ግን ጌታ እንዲህ ይላል፥ በኃያላን ᵛየተማረኩትም እንኳን ይወሰዳሉ፣ የጨካኞችም አደን ያመልጣል፤ ^ኃያሉ አምላክ የቃል ኪዳን ህዝቡን ሐያድናልና። ጌታም እንዲህ ይላል፥ ከእናንተ ጋር የሚጣሉትን እጣላቸዋለሁ—

፲፰ እናም አስጨናቂዎችሽን ስጋቸውን አስበላቸዋለሁ፤ እናም እንደጣፋጭ ወይን ጠጅ ደማቸውን ጠጥተው ይሰክራሉ፤ እናም ስጋ ለባሹም ሁሉ እኔ ጌታ መድኃኒትሽና ᵛቤዛሽ የያዕቆብ ^ኃያል እንደሆንኩ ያውቃሉ።

ምዕራፍ ፯

ያዕቆብ ከኢሳይያስ ማንበቡን ቀጠለ፥ ኢሳይያስ እንደ መሲሁ ይናገራል—መሲሁ የተማሩ ሰዎች ልሳን ይኖረዋል—ለሚገርፉት ጀርባውን ይሰጣል—እርሱ አያፍርም—ኢሳይያስ ፯ን አነጻፅሩ። ፭፤፮–፭፤፯ ም.ዓ. ገደማ።

፩ አዎን፣ ጌታ እንዲህ ይላል—ፈትቻች ኋለሁን፣ ወይንስ ለዘለዓለም ወርውሬአች ኋለሁ? ጌታ እንዲህ ይላል—እናታችሁን የፈታሁበት የፍቺዋ ፅህፈት የት አለ? ለማን ነው አሳልፌ የሰጠኋችሁ? ወይስ እናንተን ᵛየሸጥኩት ከአበዳሪዎች ለየትኛው ነው? አዎን፣ ለማን ሸጥኳችሁ? እነሆ፣ ስለኃጢአታችሁ ራሳችሁን ሸጣችኋል፣ እናም ስለመተላለፋችሁ እናታችሁም ተፈታለች።

፪ ስለሆነም፣ እኔ ስመጣ ማንም ሰው አልነበረም፤ ᵛበምጣራበትም ጊዜ አዎን፣ የሚመልስ አልነበረም። የእስራኤል ቤት ሆይ፣ መታደግ እንዳትችል እጄ ፈፅሞ አጥራለች፣ ወይስ ለማዳን ኃይል የለኝምን? እነሆ በግሰጻዬ ^ባህሩን አደርቃለሁ፣ ሐወንዞችንም ምድረበዳ አደርጋለሁ እናም ᵐአሳዎቻቸው ውሃው በመድረቁ ይገማሉ፣ እናም በጥማት ይሞታሉ።

፲፪ ለ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ—የዲያብሎስ ቤተክርስቲያን።
ሐ ቅ.መ.መ. የአብርሐም ቃል ኪዳን።
፲፫ ሀ ፫ ኔፊ ፳፪ ፡ ፬።
ለ ኢሳ. ፶ ፡ ፴፩፤ ፩ ኔፊ ፳፩ ፡ ፳፫፤ ት. እና ቃ. ፻፴፫ ፡ ፶፯።
፲፬ ሀ ኢሳ. ፲፩ ፡ ፲፩፤ ፪ ኔፊ ፳፭ ፡ ፲፯፤ ፳፱ ፡ ፩።
ለ ፩ ኔፊ ፳፪ ፡ ፲፫–፲፬።
ሐ ፪ ኔፊ ፫ ፡ ፭።
፲፭ ሀ ያዕቆ. ፮ ፡ ፫።
ለ ት. እና ቃ. ፻፲፯ ፡ ፳፪–፳፮።
ሐ ፪ ኔፊ ፣ ፡ ፲፯፤ ፳፰ ፡ ፲፭፤ ፫ ኔፊ ፲፯ ፡ ፳።
ቅ.መ.መ. የመጨረሻ ቀናት፣ የጓለኛው ቀናት።
፲፯ ሀ ኢሳ. ፶፱ ፡ ፳፩–፳፯።
ለ ይህም በቁጥር ፲፯ ውስጥ እንደተጠቀሰው የጌታ የቃል ኪዳን ህዝብ ማለት ነው።
፲፯ ሀ ፩ ኔፊ ፳፭ ፡ ፳፭።
ለ ቅ.መ.መ. ያህዌህ።
ሐ ፪ ነገሥ. ፲፯ ፡ ፴፱።
፲፰ ሀ ቅ.መ.መ. መድኃኒት።
ለ ዘፍጥ. ፶፱ ፡ ፳፬፤ ኢሳ. ፳ ፡ ፲፯።
፲፯ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. ክህደት።
፪ ሀ ምሳ. ፩ ፡ ፳፩–፳፫፤ ኢሳ. ፳፫ ፡ ፲፪፤ አልማ ፭ ፡ ፴፯።
ለ ዘፀአ. ፲፡ ፡ ፳፩፤ መዝ. ፻፯ ፡ ፤ ት. እና ቃ. ፻፴፫ ፡ ፳፳–፳፱።
ሐ ኢያ. ፫ ፡ ፲፭–፲፯።
መ ዘፀአ. ፯ ፡ ፳፩።

፲ ሰማያትን ᵐጥቁረት አለብሳቸዋለሁ፣ እናም መሸፈኛቸውን ᵃማቅ አደርጋለሁ።

፡፡ የእስራኤል ቤት ሆይ ጌታ እግዚአ ብሔር በትክክለኛው ጊዜ ለእናንተ እን ዴት መናገር እንድችል የተማሩትን ᵐልሳን ሰጥቶኛል። እናንተ በደከማችሁ ጊዜ ማለዳ በማለዳ ያነቃችኋል። እንደተማሪ እንድሰማ ጆሮዬን ያነቃቃል።

፡፡ ጌታ እግዚአብሔር ᵐጆሮዬን ከፍቷል፣ እናም እኔ አመፀኛ አልነበርኩም፣ ወደኋ ላም አልተመለስኩም።

፡፡ ጀርባዬን ᵐለገራፊዎች፣ እናም ጉንጭ ንም ለፀጉር ነጪዎች ሰጠሁ። ፊቴንም ከውርደትና ከተፋት አልመለስኩም።

፡፡ ጌታ እግዚአብሔር ይረዳኛል፣ ስለ ዚህም አላፍርም። ስለዚህ ፊቴን እንደባ ልጩት ድንጋይ አድርጌዋለሁ፣ እናም እን ደማላፍር አውቃለሁ።

፡፡ እናም ጌታ ቅርቤ ነው፣ እርሱም ያጸድ ቀኛል። ከእኔ ጋር የሚከራከር ማነው? በአ ንድነት እንቁም። ጠላቴስ ማነው? ወደ እኔ እንዲቀርብ ፍቀዱለት እናም በአፌ ኃይለ ቃል እመታዋለሁ።

፡፡ ጌታ እግዚአብሔር ይረዳኛል። እናም እኔን ᵐየሚኮንኑ ሁሉ፣ እነሆ፣ ሁሉ እንደ ልብስ ያረጃሉ፣ እናም ብል ይበላቸዋል።

፡ ከእናንተ መካከል ጌታን የሚፈራ፣ የአገልጋዩን ᵐድምፅ የሚታዘዝ፣ በጨ ለማ የሚራመድ እንዲሁም ብርሃን የሌ ለው ማነው?

፡፡ እነሆ እናንተ እሳት የምታነዱ ሁሉ፣ የእሳትንም ወላፈን የምትጭሩ፣ ᵐበእሳታ ችሁ ብርሃን እና ባነደዳችሁት ወላፈን ተመ ላለሱ። ይህ ከእጄ ይሆንባችኋል—በሀዘንም ትሞታላችሁ።

ምዕራፍ ፳

ያዕቆብ ከኢሳይያስ ማንበብ ቀጠለ፥ በመ ጨረሻዎቹ ቀናት፣ ጌታ ፅዮንን ያፅናናል እንዲሁም እስራኤልን ይሰበስባል—የዳኑ ትም ወደ ፅዮን በታላቅ ደስታ ተከበው ይመጣሉ—ኢሳይያስ ፲፭ እና ፲፰፡ ፭–፪ን አነጻፅሩ። ከ፳፻፹፱–፳፻፺፭ ም.ዓ. ገደማ።

፡ እናንተ ፅድቅን የምትከተሉ ስሙኝ። የተቆረጣችሁበትን ᵐድንጋይ፣ እንዲሁም የተቆፈራችሁበትን ጉድጓድ ተመልከቱ።

፡ ወደ ᵐአባታችሁ አብርሃምና ወደ ወለ ደቻችሁ ᵃሣራ ተመልከቱ፤ ብቻውን ጠራ ሁት፣ እናም ባረክሁትም።

፡ ጌታ ᵐፅዮንን ያፅናናል፣ በእርሷ ባድማ የሆነውን ቦታ ሁሉ ያፅናናል፤ እናም ᵃምድ ረበዳዋንም እንደ ዔድን፣ እናም በረሃዋን እንደ ጌታ የአትክልት ስፍራ ያደርገዋል። ደስታና ተድላ፣ ምስጋና እና የዝማሬ ድምፅ ይገኝባታል።

፡ ሕዝቤ ሆይ፥ አድምጡኝ፤ ወገኔ ሆይ፣ ስሙኝ፤ ᵐህግ ከእኔ ይወጣልና፣ እና ፍርዴን ለህዝብ እንደ ᵃብርሃን እንዲያርፍ አደርጋለሁ።

፡ ፅድቄ ቀርቧል፤ ᵐማዳኔም ወጥቷል፣ እናም ክንዴ በህዝቡ ይፈርዳል። ᵃደሴቶች እኔን ይጠባበቃሉ፣ እናም በክንዴ ይታ መናሉ።

፡ ዐይኖቻችሁን ወደ ᵐሰማያት አንሱ፣ እናም ወደታች ወደ ምድር ተመልከቱ፤ ሰማያት እንደጢስ በንነው ᵃይጠፋሉ፣ ምድርም እንደልብስ ᶜታረጃለች፤ እናም የሚኖሩባት እንዲሁ ይሞታሉ። ነገር ግን ማዳኔ ለዘለዓለም ይሆናል፣ ፅድቄም አይ ፈርስም።

፲ ሀ ዘፀአ. ፲፡ ፳፭።
ለ ራዕ. ፮፡ ፲፪።
፡ ሀ ሉቃ. ፪፡ ፴፯–፴፯።
፡ ሀ ት. እና ቃ. ፶፡ ፩።
፡ ሀ ማቴ. ፳፯፡ ፳፯፣
፪ ኔፊ ፱፡ ፳።
፡ ሀ ሮሜ ፰፡ ፴፩።
፡ ሀ ት. እና ቃ. ፩፡ ፴፰።
፡ ሀ መሳ. ፲፯፡ ፮።
፡ ሀ ቅ.መ.መ. አለት።
፡ ሀ ዘፍጥ. ፲፯፡ ፩–፰፣
ት. እና ቃ. ፻፴፪፡ ፴፱።
ለ ዘፍጥ. ፳፡ ፲፯።
፡ ሀ ቅ.መ.መ. ፅዮን።
ለ ኢሳ. ፴፭፡ ፩–፪፣ ፮–፯።
፡ ሀ ወይም ትምህርት።
ኢሳ. ፪፡ ፫።
ቅ.መ.መ. ወንጌል።
ለ ቅ.መ.መ. ብርሀን፣
የክርስቶስ ብርሀን።
፡ ሀ ቅ.መ.መ. ደህንነት።
ለ ፪ ኔፊ ፲፡ ፳።
፡ ሀ ፪ ጴጥ. ፫፡ ፲።
ለ ዕብ. መበተን።
መዝ. ፻፪፡ ፳፭–፳፯።
ሐ ዕብ. መበስበስ።

፲ ፅድቅን የምታውቁ፣ ህጌንም በልባ
ችሁ የፃፍኩባችሁ እኔን አድምጡኝ፣ የሰ
ዎችን ዘለፋ አትፍሩ፣ ወይም ስድባቸው
ንም ᵐአትፍሩ።
፲፩ እንደልብስም ብል ይበላቸዋልና፣
እናም ትል እንደሱፍ ይበላቸዋል። ነገር
ግን ፅድቄ ለዘለዓለም፣ እናም ማዳኔ ከት
ውልድ ወደ ትውልድ ይሆናል።
፲፪ የእግዚአብሔር ክንድ ሆይ ተነስ! ተነስ!
ᵐኃይልንም ልበስ፣ እንደጥንቱ ቀናት
ተነሳ። ረዓብን የቆራረጥክ፣ ዘንዶውንም
የወጋህ አንተ አይደለህምን?
፲፫ ባህሩን፣ የታላቁን ጥልቅ ውሃ ያደ
ረቅህ፣ የዳኑትም ይሻገሩ ዘንድ ጥልቁን
ባህር ᵐመንገድ ያደረግህ አንተ አይደለህ
ምን?
፲፬ ስለዚህ፣ ጌታ ᵐያዳናቸው ይመለሳሉ፣
ᵃበዝማሬም ወደ ፅዮን ይመጣሉ፤ እናም የዘ
ለዓለም ደስታና ቅዱስነት በራሳቸው ላይ
ይሆናል፤ እናም ደስታና ተድላን ያገኛሉ፤
ሀዘንና ሐልቅሶም ይሸሻሉ።
፲፭ ᵐእኔ እርሱ ነኝ፤ የማፅናናችሁ እኔ
ነኝ። እነሆ፣ የሚሞተውን ሰውና ᵃእንደ
ሳርም የሚሆነውን የሰው ልጅ ᵇትፈራ ዘንድ
አንተ ማን ነህ?
፲፮ እናም ሰማያትን የዘረጋውንና፣ የም
ድርን መሰረት የሰራውን፣ ጌታ ፈጣሪህን
ᵐረሳህ፣ እናም ሊያጠፉህ የተዘጋጁ ይመ
ስል በአስጨናቂዎችህ ቁጣ ምክንያት ሁል
ጊዜ ቀኑን ሁሉ ፈራህ? እናም የአስጨናቂ
ዎችህ ቁጣ የት አለ?
፲፯ ምርኮኛ እንዲፈታ፣ እና እርሱ
በጉድጓድ እንዳይሞት፣ ወይም እንጀራም
አይጐድልበት ይፈጥናል።
፲፰ ነገር ግን ሞገዱም እንዲተምም ባሕ
ርን ᵐየማናውጥ ጌታ እግዚአብሔር እኔ ነኝ፤
ስሜም የሰራዊት ጌታ ነው።
፲፱ እናም ሰማያትን እዘረጋና ምድርንም
እመሰርት ዘንድ፣ እናም ለፅዮን፣ እነሆ፣
አንቺ ᵐህዝቤ ነሽ እንድላት ቃሌን በአፍህ
አድርጌአለሁ፣ እንዲሁም በእጄ ጥላ ጋርጄ
ሃለሁ።
፲፲ ከጌታ እጅ ᵐየቁጣውን አተላ ᵃበፅዋ
የጠጣሽ ኢየሩሳሌም ሆይ ንቂ፣ ንቂ፣
ቁሚ፣ ከሚያንገደግድ ዋንጫ መራራን
ጠጥተሻል—
፲፳ እናም ከወለደቻቸው ወንዶች ልጆች
ሁሉ መካከል የሚመራትም የለም፤ ካሳደ
ገቻቸውም ልጆች ሁሉ እጅዋን የሚይዝ
የለም።
፲፱ እነዚህ ሁለቱ ᵐወንዶች ልጆች ወደ
አንቺ ይመጣሉ፣ ላንቺ ማን ያዝንልሻል—
መደምሰስሽና መውደምሽ፣ ረሃብና
ሰይፍም—እንዲሁም በማን አፅናናሻለሁ?
፳ ከእነዚህ ከሁለቱ በስተቀር ወንዶች
ልጆችሽ ዝለዋል፤ በአደባባይ ላይ ተኝተ
ዋል፤ በወጥመድ እንዳለ የሜዳ ኮርማ በጌታ
ቁጣ፣ በአምላክሽ ተግሳፅ ተሞልተዋል።
፳፩ ስለዚህ አሁን ይህን ስሚ፣ አንቺ ተሰ
ቃዩና ያለ ወይን ጠጅ ᵐየሰከርሽ፥
፳፪ ጌታሽ ይላል፣ ጌታ እና አምላክሽ የወ
ገኑ ጉዳይ ᵐይማፀናል፤ እነሆ፣ የሚያንገደ
ግድን ፅዋ፣ የቁጣዬንም ዋንጫ አተላውን
ከእጅሽ ወስጃለሁ፣ ደግመሽም ከእንግዲህ
አትጠጪውም።
፳፫ ነገር ግን ነፍስሽን እንሻገር ዘንድ ዝቅ
በይ በሚሉት በአስጨናቂዎችሽ እጅ ᵐአኖ
ረዋለሁ፥ እናም ሰውነትሽንም ለሚሻገሩ
በት እንደ መሬት መንገድ አድርገሽ ዘር
ግተሽዋል።

፲ ሀ መዝ. ፻፲፡፱፣ ፲፩፣
ት. እና ቃ. ፻፳፪፡፱።
፱ ሀ ት. እና ቃ. ፻፲፫፡፲–፳።
፲ ሀ ኢሳ. ፴፭፡፳።
፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. ቤዛ፣ ማዳን፣
ቤዛነት።
ለ ኢሳ. ፴፭፡፲።
ሐ ራዕ. ፳፩፡፱።
፲፪ ሀ ት. እና ቃ. ፻፴፫፡፴፯፣
፻፴፯፡፳፪።
ለ ኢሳ. ፶፣ ፲–፳፣
፩ ጴጥ. ፩፡፳፬።
ሐ ኤር. ፩፡፳።
፲፫ ሀ ኤር. ፳፣፡፳፯።
፲፭ ሀ ፩ ኔፊ ፱፡፪።
፲፮ ሀ ፪ ኔፊ ፣፡፪፣ ፳፱፡፲፱።
፲፯ ሀ ሉቃ. ፳፩፡፳፬።
ለ ኢሳ. ፳፱፡፱፣
ኤር. ፳፭፡፲፭።
፲፱ ሀ ራዕ. ፲፩፡፣።
፳፩ ሀ ፪ ኔፊ ፳፯፡፱።
፳፪ ሀ ኤር. ፶፡፴፬።
፳፫ ሀ ዘካ. ፲፪፡፱።

፲፩ ᵐፅዮን ሆይ ᵃንቂ፣ ንቂ ᵇሀይልሽን ልበሺ፤ ቅድስት ከተማ ኢየሩሳሌም ሆይ፣ ቆንጆ ልብስሽን ልበሺ፤ ያልተገረዘና እር ኩስ ከእንግዲህ ᵐአይገባብሽምና።

፲፪ ትቢያን አራግፊ፤ ኢየሩሳሌም ሆይ፣ ᵐተነሺ፣ ተቀመጪ፤ ምርኮኛይቱ የፅዮን ሴት ልጅ ሆይ የአንገትሽን ᵃእስራት እራ ስሽ ፍቺ።

ምዕራፍ ፱

አይሁዶች በቃልኪዳናቸው ምድር ላይ ሁሉ እንደሚሰበሰቡ ያዕቆብ ገለጸ—የኃጢያት ክፍያው ለሰው ከውድቀት ቤዛ ይሆናል—የሙታን አካል ከመቃብር እንዲሁም መንፈሳቸው ከሲኦልና ከገነት ይመጣል—ይፈረድባቸዋል—የኃጢያት ክፍያው ከምት፣ ከሲኦል፣ ከዲያብሎስ፣ ማለቂያ ከሌለው ስቃይ ያድናል—ፃድ ቃን በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ ይድናሉ—የኃጢያት ቅጣቶች ተገልፆ አል—የእስራኤሉ ቅዱስ የመግቢያው በር ጠባቂ ነው። ከ፳፻፶፯–፳፻፶፰ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም አሁን የተወደዳችሁ ወንድሞቼ፣ ጌታ ከእስራኤል ቤት ሁሉ ጋር የገባውን ᵐቃል ኪዳን ታውቁ ዘንድ እኔ እነዚህን ነገ ሮች አንብቤአለሁ—

፪ እናም እርሱ ከመጀመሪያው ጀምሮ፣ ከትውልድ እስከ ትውልድ፣ ወደ እውነ ተኛው ቤተ ክርስቲያንና ወደ እግዚአብ ሔር እቅፍ ᵐደግመው እስከሚመጡ ድረስ፣ እነርሱ ወደ ቤታቸው ወደ ᵃርስት ምድ ራቸው በሚሰበሰቡበትና የቃልኪዳናቸው ምድር ሁሉ ᵇበሚመሰርቱበት ጊዜ ለአ ይሁድ በቅዱስ ነቢያቱ አፍ እንደተናገረ አንብቤአለሁ።

፫ እነሆ፣ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ፣ እነ ዚህን ነገሮች ለእናንተ የምናገረው ጌታ እግ ዚአብሔር በልጆቻችሁ ላይ ባፈሰሰበት በረ ከት ምክንያት እንድትደሰቱና ራሳችሁን ለዘለዓለም ᵐእንድታነሱ ነው።

፬ ከእናንተ ብዙዎቹ ወደፊት ስለሚ መጡ ነገሮች ለማወቅ ብዙ እንደመረመ ራችሁ አውቃለሁ፤ ስለዚህ ስጋችን እር ጅቶ ከዚያም እንደሚሞት እንደምታው ቁም አውቃለሁ፣ ይሁን እንጂ፣ ᵐበአካላ ችን እግዚአብሔርን እናያለን።

፭ አዎን፣ እኛ ከመጣንበት በኢየሩሳሌም ውስጥ ላሉት እራሱን በአካል እንደሚያሳይ እንደምታውቁ አውቃለሁ፤ በእነርሱ መካ ከል ይህ መሆኑ አስፈላጊ ነውና፤ ምክንያ ቱም ታላቁ ᵐፈጣሪው ሁሉም ሰዎች ለእርሱ ይገዙ ዘንድ እርሱ ለሰው ልጆች በስጋ ለመ ገዛት እንዲፈቅድና፣ ለሰዎች ᵃሁሉ ይሞት ዘንድ አስፈላጊ ነበረበት።

፮ ምህረት የተሞላበት የታላቁ የፈጣሪ ᵐዕቅድ ይፈጸም ዘንድ፣ ሞት በሰው ልጆች ላይ ስለመጣ፣ ᵃየትንሣኤ ኃይል ይኖር ዘንድ ያስፈልጋል፣ ᵇበውድቀት የተነሳ ትንሣኤ ለሰው መምጣቱ አስፈላጊ ነው፣ እናም ውድቀት የመጣው በመተላለፍ ምክ ንያት ነው፤ እና ሰውም በመውደቁ ምክን ያት ከጌታ ፊት ᶜተለይቷል።

፯ ስለዚህ፣ ᵐወሰን የሌለው ᵃየኃጢያት

ᶻ፲፩ ᵐ ቅ.መ.መ. ፅዮን።
ᵃ ኢሳ. ፶፪፡፩–፪።
ᵇ ት. እና ቃ. ፲፲፫፡፲–ᶻ፡ᶻ–ᶻᶻ።
ᶜ ኢዩ. ፫፡፲፯።
ᶻᶻ ᵐ ይህም በመጨረሻም በመዳን፣ ከአፈር ተነሳ እናም በክብር ተቀመጥ ማለት ነው።
ᵃ ት. እና ቃ. ፲፲፫፡፱–፲።
፱ ᵃ ᵐ ቅ.መ.መ. የአብርሐም ቃል ኪዳን።
ᵇ ᵐ ፪ ኔፊ ፮፡፲ᶻ።
ᶜ ᵐ ቅ.መ.መ. የወንጌል ዳግም መመለስ።
ᵈ ᵐ ፪ ኔፊ ፲፡ᶻ–ᶻᶻ። ቅ.መ.መ. የቃል ኪዳን ምድር።
ᵉ ᵐ ቅ.መ.መ. እስራኤል—የእስራኤል መሰብሰብ።
፫ ᵐ ᵐ ጆ.ስ.ት. መዝ. ᶻᶻ፡ᶻ–ᶻ (ተጨማሪ)።
፬ ᵐ ኢዮብ ፲፱፡ᶻᶻ፣ አልማ ፲ᶻ፡ᶻᶻ–ᶻᶻ፣ ᶻᶻᶻ፡ᶻᶻ፣ ሄለ. ፲፫፡፲ᶻ፣ ሞር. ፱፡፲፫።
ᶻ ᵐ ቅ.መ.መ. መፍጠር፣ ፍጥረት።
ᵃ ዮሐ. ፲ᶻ፡ᶻᶻᶻ፣ ᶻᶻᶻ፡ᶻ፣ ᶻᶻ ኔፊ ᶻᶻᶻ፡ᶻᶻᶻ፣ ᶻᶻᶻ፡ᶻᶻ፣ ᶻᶻ ኔፊ ᶻᶻᶻ፡ᶻᶻ–ᶻᶻ።
ᶻᶻ ᵐ ᵐ ቅ.መ.መ. ትንሣኤ።
ᵃ ቅ.መ.መ. ትንሣኤ።
ᵇ ቅ.መ.መ. የአዳም እና የሔዋን ውድቀት።
ᶜ ᶻᶻ ኔፊ ᶻ፡ᶻ።
ᶻᶻᶻ ᵐ አልማ ᶻᶻᶻ፡ᶻ።
ᵃ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ።

ክፍያ ይኖር ዘንድ ያስፈልጋል—በዚህ ወሰን በሌለው የኃጢያት ክፍያ ባይሆን ኖሮ ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን አይለ ብስም ነበር። ስለዚህ፣ በሰው ላይ የመጣው ሐየመጀመሪያው ፍርድ ለዘለዓለም መየሚ ቆይ መሆን ነበረበት። እናም እንዲህ ቢሆን ኖሮ ይህ ስጋ ሞቶ፣ በስብሶ፣ ተበታትኖ ወደ እናት ምድሩ በመመለስ፣ በድጋሚ ሳይነሳ በቀረ ነበር።

፳ አቤቱ የእግዚአብሔር ᵇጥበብ፣ ᵃምህ ረቱና ሐፀጋው! እነሆም፣ ᵐስጋ የማይ ነሳ ቢሆን ኖሮ መንፈሳችን ከዘለዓለማ ዊው አምላክ ፊት ተነጥሎ ዳግም እንዳይ ነሳ ᵐከተጣለውና ᶜዲያብሎስ ለሆነው መል አክ ተገዢዎች ይሆኑ ነበር።

፳፩ እናም መንፈሶቻችን እንደርሱ ሊሆኑ በተገባቸው ነበር፣ እናም እኛ ዲያብሎሶች፣ ለዲያብሎስ ᵇመላእክቶች በመሆን ከአምላ ካችን ፊት ᵃየጠፋንና፣ ሐከሀሰት አባት ጋር፣ በችግር፣ ልክ እንደእርሱ የቀረን እንሆን ነበር፤ አዎን፣ በዚያ የመጀመሪያ ቤተሰ ቦቻችንን ᵐእንዳታለለው፣ እራሱን እን ደብርሃን ᵐመልአክ እንዲመስል ራሱም ᶜእንደቀየረውና፣ የሰው ልጆችን በግድያ ᵃሚስጥራዊ ሴራዎች እና በሁሉም የጨ ለማ ሚስጥር ስራዎች እንደሚበጠብጠው እንሆን ነበር።

፲ አቤቱ፣ ከዚህ ከሚያስቀይመው አስ ፈሪ እቅፉ፣ አዎን፣ እኔ የስጋ ሞት፣ እናም ደግሞ የመንፈስ ሞት ብዬ የምጠራው ያ አስፈሪ ᵇሞትና ᵃሲኦልን ሊያስመልጠን መንገዱን ያዘጋጀልን የአምላካችን ጥሩነት እንዴት ታላቅ ነው።

፲፩ እናም የእኛ አምላክ የእስራኤል ቅዱስ ᵇማምለጫውን መንገድ ስላዘጋጀልን፣ ጊዜ ያዊ የሆነው እኔ የተናገርኩት ይህ ᵃሞት፣ ሙታኖቹን ያስረክባል፤ ይህም ሞት መቃ ብር ነው።

፲፪ እናም መንፈሳዊ ሞት የሆነው ይህ እኔ የተናገርኩት ᵇሞት፣ ሙታኖቹን ያስ ረክባል፤ ይህም መንፈሳዊ ሞት ᵃሲኦል ነው፤ ስለዚህ፣ ሞትና ሲኦል ሙታኖቻ ቸውን ማስረከብ አለባቸው፣ እናም ሲኦል የያዛቸውን መንፈሶች ማስረከብ አለበት፣ መቃብርም የያዘቻቸውን አካላት ማስ ረከብ አለባት፣ እናም የሰዎች ስጋና ሐመን ፈስ አንዱ ወደ ሌላው ᵐደግሞ ይመለሳል፤ ይህም በእስራኤል ቅዱስ የትንሳኤ ሀይል ነው።

፲፫ አቤቱ የአምላካችን ᵇዕቅድ እንዴት ታላቅ ነው! በሌላው በኩል፣ የእግዚአ ብሔር ᵃገነት የቅዱሳንን መንፈስ ማስ ረከብ አለባት፤ መቃብርም የፃድቃንን ስጋ ታስረክባለች፤ እናም ስጋና መንፈስ እንደነ በሩ ሐበድጋሚ ይገጣጠማሉ፣ ሁሉም ሰዎች የማይበሰብሱና፣ ᵐየማይሞቱ ይሆናሉ፣ እና የእኛም ᵐእውቀት ᶜፍፁም ከመሆኑ በቀር፣ እነርሱም ልክ እንደእኛ በስጋ ፍፁም እው ቀት ያላቸው ነፍሳት ይሆናሉ።

፲፬ ስለዚህ፣ ᵇስለስህተቶቻችን ሁሉና፣

ᶠ ሐ ሞዛያ ፲፯፡፱–፳፡ አልማ ᶻᶠᶠ፡ᶠ፣ ᶠᶠ፣ ᶠᶠᶠ።
ᵐ ሞዛያ ፲፭፡፲ᶠᶠ።
ᶜ ᵇ ኢዮብ ፲ᶠᶠ፡፲ᶠᶠ፣ አብር. ᶠ፡ᶜᶜᶠ።
ቅ.መ.መ. ጥበብ።
ᵃ ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።
ሐ ቅ.መ.መ. ጸጋ።
ᵐ ት. እና ቃ. ᶻᶠᶠ፡ᶻᶠᶠ–ᶻᶠᶠ።
ᵃ ኢሳ. ፲ᶠ፡፲ᶠᶠ፣ ᶠ ኔፊ ᶠᶠ፡፲ᶠ–፲ᶜᶜ፣ ሙሴ ᶠ፡ᶠ–ᶠ፣ አብር. ᶠ፡ᶜᶜᶠ–ᶜᶜᶜ።
ᶜ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
ᶠᶠ ᵇ ያዕቆ. ᶠ፡፲ᶠᶠ፣ አልማ ᶠᶠ፡ᶜᶜᶠ፣ ᶠᶠᶠᶠ።
ᵃ ራዕ. ፲ᶠᶠ፡ᶠ–ᶠᶠ።
ሐ ቅ.መ.መ. ሐሰት።
ᵐ ዘፍጥ. ᶠ፡ᶠ–፲ᶠ፣ ሞዛያ ፲ᶠᶠ፡ᶠ፣ ሙሴ ᶠ፡ᶠ–፲ᶠᶠ።
ᵃ ት. እና ቃ. ᶠᶜᶜᶠ፡ᶜᶜ።
ᶜ ᶠ ቆሮ. ፲ᶠᶠ፡፲ᶠᶠ፣ አልማ ᶠᶠ፡ᶠᶠᶠ።
ᵃ ቅ.መ.መ. የሚስጥር ስብሰባ።
ᶠ ᵇ ሞዛያ ፲ᶠᶠ፡ᶠ–ᶜ፣ አልማ ᶻᶠᶠ፡ᶠ–ᶠᶠ፣ ᵃ ቅ.መ.መ. ሲያል።
ᶠᶠᶠ ᵇ ቅ.መ.መ. መድኃኒት።
ᵃ ቅ.መ.መ. ስጋዊ ሞት።
ᶠᶠᶠ ᵇ ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ሞት።
ᵃ ት. እና ቃ. ᶜᶜᶠ፡ᶠᶜᶠ–ᶠᶜᶠ።
ሐ ቅ.መ.መ. መንፈስ።
ᵐ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
ᶠᶠᶠ ᵇ ቅ.መ.መ. የቤዛነት ዕቅድ።
ᵃ ት. እና ቃ. ᶠᶠᶠᶜ፡ᶠᶠᶠ–ᶠᶠᶠ። ቅ.መ.መ. ገነት።
ሐ አልማ ᶠᶠᶠ፡ᶠᶠᶠ።
ᵐ ቅ.መ.መ. የማይሞት፣ አለሟችነት።
ᶜ ት. እና ቃ. ᶠᶠᶠ፡ᶠᶜᶠ–ᶠᶠᶠ።
ᶜ ቅ.መ.መ. ፍጹም።
ᶠᶠᶠ ᵇ ቅ.መ.መ. በደል።

ንፁህ አለመሆናችንን፣ እናም ^ስለራቁ ትነታችን ፍፁም ሐእውቀት ይኖረናል፤ ™ጻድቃንም ™ንፅህናን ^ለብሰው የጽድቅ ^መጎናፀፊያ ተደርቦላቸው ስለደስታቸ ውና ጻድቅነታቸው ፍፁም እውቀት ይኖ ራቸዋል።

፲፭ እናም እንዲህ ይሆናል ሁሉም ሰዎች ከዚህ ከመጀመሪያው ሞት ወደ ሕይወት ሲ.ያልፉና፣ ህያዋን ሲሆኑ፣ በእስራኤል ቅዱስ ™የፍርድ ወንበር ፊት መምጣት አለ ባቸው፤ እናም ከዚያ ^ፍርዱ ይመጣል፣ ከእዚያም በኋላ በእግዚአብሔር ቅዱስ ፍርድ መሰረት ይፈረድባቸው ይገባል።

፲፮ እናም በእርግጥ፣ ጌታ ህያው እንደ ሆነ፣ ጌታ አምላክ ተናግሮታልና፣ እናም ይህ የእርሱ ™ሳይከናወን የማይቀር ዘለዓ ለማዊ ^ቃሉ ነው፣ ፃድቅ የሆኑት አሁ ንም ፃድቅ ይሆናሉ፣ ሐየረከሱትም አሁ ንም ™ርኩሳን ይሆናሉ፤ ስለዚህ፣ የረከሱት ™ዲያብሎስና መላዕክቱ ናቸው፤ እነርሱም ደግሞ ለእነርሱ ወደ ተዘጋጀላቸው ወደ ^ዘለዓለማዊ እሳት ይሄዳሉ፤ እናም ስቃያ ቸው እሳቱ ወደላይ ለዘለዓለም እንደሚነሳ ወላፈን፣ መጨረሻ እንደሌለው በዲን እን ደሚቃጠል ^የእሳት ባህር ይሆናል።

፲፯ አቤቱ የአምላካችን ™ፍትህና ታላቅ ነት እንዴት ታላቅ ነው! እርሱ ቃሉን ሁሉ ይፈፅማል፣ እነርሱም ከአፉ ወጥተዋል፣ እናም የእርሱ ህግ መፈፀም አለበት።

፲፰ ነገር ግን፣ እነሆ፣ ፃድቃን፣ የእስ ራኤሉ ቅዱስ ™ቅዱሳኖች፣ በእስራኤሉ ቅዱስ ያመኑት፣ የዓለምን ^መስቀሎች የታገሱ፣ እፍረቷንም የናቁ፣ እነዚህ ሐከዓ ለም መጀመሪያ ጀምሮ የተዘጋጀላቸውን የእግዚአብሔርን ™መንግስት ™ይወርሳሉ፣ እናም ደስታቸው ^ለዘለዓለም ሙሉ ይሆ ናል።

፲፱ አቤቱ የአምላካችን የእስራኤል ቅዱስ ታላቅነትና ምህረት እንዴት ታላቅ ነው! እርሱ ቅዱሳኑን ከሚያስቀይመው ™ከአስ ፈሪው ዲያብሎስና፣ ከሞትና፣ ^ከሲኦል፣ እናም ከዚያ መጨረሻ የሌለው ስቃይ ከሆ ነው በዲን ከሚቃጠለው የእሳት ባህር ሐአድኗቸዋልና።

፳ አቤቱ የአምላካችን ™ቅዱስነት እንዴት ታላቅ ነው! እርሱ ሁሉን ነገሮች ^ያውቃ ልና፣ እናም እርሱ ከሚያውቀው በስተቀር ምንም ነገር የለም።

፳፩ እናም እርሱ ሰዎች ሁሉ የእርሱን ድምፅ የሚያዳምጡ ከሆነ ™ሊያድናቸው ዘንድ ወደ እዚህ ዓለም ይመጣል፤ እነሆም፣ እርሱ በሁሉ ሰዎችን ^ህመም፣ አዎን፣ ሐበአዳም ቤተሰብ አባል በሆኑት በእያንዳ ንዱ ሕያው ፍጥረታት፣ በወንድም፣ በሴ ትም፣ በልጆችም ህመም ይሰቃያል።

፳፪ እናም እርሱ ይህን ሁሉ የሚሰቃየው ትንሣኤ በሰው ልጆች ሁሉ ላይ ያልፍ ዘን ድና፣ ሁሉም በእርሱ ፊት በታላቁና በፍ ርድ ቀን ይቆሙ ዘንድ ነው።

፳፫ እናም እርሱ ሁሉም ሰዎች፣ በእስራ

፲፩ ^ ሞር. ፱፡፭።
ሐ ሞዛያ ፫፡፳፭፣ አልማ ፭፡፲፰።
መ ቅ.መ.መ. ጻድቅ፣ ጽድቅ።
ሠ ቅ.መ.መ. ንጹህ፣ ንጹህነት።
ረ ምሳ. ፴፩፡፳፭።
ሰ ት. እና ቃ. ፲፱፡፫፲፯።
፲፭ ™ ቅ.መ.መ. ፍርድ፣ የመጨረሻው።
ለ መዝ. ፲፱፡፱፣ ፪ ኔፊ ፴፡፱።
፲፯ ™ ት. እና ቃ. ፶፯፡፲፭።
ለ ፩ ነገሥ. ፰፡፶፣ ፶፯፡፣ ት. እና ቃ. ፩፡ ፴፰፡ ሙሴ ፩፡፴።
ሐ ቅ.መ.መ. እድፍ፣ እድፍነት።
መ ፩ ኔፊ ፲፭፡ ፴፣–፴፭፣ አልማ ፯፡ ፳፩፣ ሞር. ፱፡ ፲፱፣ ት. እና ቃ. ፹፰፡ ፴፭።
ሠ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
ረ ሞዛያ ፳፯፡ ፳፡ ፳፣ ሰ ራዕ. ፳፩፡ ፰፣ ፪ ኔፊ ፳፡ ፳፣ ት. እና ቃ. ፰፡ ፲፣ ፲፯።
፲፯ ™ ቅ.መ.መ. ፍትህ።
፲፰ ™ ቅ.መ.መ. ቅዱሳን።
ለ ሉቃ. ፲፩፡ ፳፯።
ሐ አልማ ፲፫፡ ፲፡
መ ቅ.መ.መ. ከፍተኛነት።
ሠ ት. እና ቃ. ፵፭፡ ፶፰፣ ፹፡ ፴፰።
ረ ቅ.መ.መ. የዘለዓለም ህይወት።
፲፱ ™ ት. እና ቃ. ፲፰፡ ፰።
ለ ቅ.መ.መ. ሲ.ያል።
ሐ ፩ ኔፊ ፲፭፡ ፴፭።
፳ ™ ቅ.መ.መ. ቅድስና።
ለ አልማ ፳፯፡ ፴፭፣ ት. እና ቃ. ፴፰፡ ፪።
፳፩ ™ ቅ.መ.መ. ደህንነት።
ለ ት. እና ቃ. ፲፰፡ ፲፩፣ ፲፱፡ ፲፡
ሐ ቅ.መ.መ. አዳም።

ኤል ቅዱስ ፍፁም የሆነ እምነት ኖሯቸው ᵐንስሀ መግባትና፣ በእርሱ ስም ᵃመጠመቅ እንዳለባቸው ያዝዛል፣ ካልሆነ ግን በእግ ዚአብሔር መንግስት ውስጥ መዳን አይ ችሉም።

፳፱ እናም በእርሱ ስም የማያምኑና ንስሀ የማይገቡ፣ ᵐበስሙም የማይጠመቁና፣ እስ ከመጨረሻው ᵃየማይጸኑ ከሆነ ግን ᵐመኮነን ይገባቸዋል፤ ምክንያቱም ጌታ አምላክ የእ ስራኤል ቅዱስ ተናግሮታልና።

፳፭ ስለዚህ፣ እርሱ ᵐህግን ሰጥቷል፤ እናም ᵃህግ ባልተሰጠበት ቅጣት የለም፤ እናም ቅጣት በሌለበት ኩነኔ የለም፤ እናም መኮነን በሌለበት በኃጢያት ክፍያው የተ ነሳ የእስራኤል ቅዱስ ምህረት በእነርሱ ላይ ውጤታማ ይሆናል፤ ምክንያቱም በእርሱ ኃይል ድነዋልና።

፳፮ ከአስቀያሚ ከአስፈሪው ከሞትና ከሲኦል፣ እናም ከዲያብሎስና፣ መጨረሻ ከሌለው በዲን ከሚቃጠለው የእሳት ባህር ስቃይ ይተርፉ ዘንድ፣ ᵐህጉ ᵃባልተሰጣቸው ሁሉ ላይ ᵐየኃጢያት ክፍያው ᵐለፍትህ የሚያስፈልገውን ሁሉ ያደርጋል፤ እናም ᵐእስትንፋስ ወደሰጣቸው እስራኤሉ ቅዱስ ወደሆነው እግዚአብሔር ይመለሳሉ።

፳፯ ነገር ግን ᵐህጉ ለተሰጠው፣ አዎን፣ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ልክ እንደ እኛ ያለው፣ እናም የሚተላለፋቸውና፣ የሙከ ራውን ጊዜ የሚያባክን ወዮለት፣ መጨረ ሻው አሰቃቂ ነውና!

፳፰ አቤቱ የክፉ የብልጠት ᵐዕቅድ! አቤቱ የሰው ᵃግብዝነትና ድክመትና፣ ሞኝ ነት! ᵐበተማሩ ጊዜ ራሳቸውን ᵐእንደብ ልህ ይቆጥራሉ፣ እናም የእግዚአብሔርን ᵐምክር የማይሰሙ፣ በራሳቸው እንደሚያ ውቁ በማሰብ፣ ይህን ችላ ይሉታልና፣ ስለ ሆነም ጥበባቸው ሞኝነታቸው ነው እና አይ ጠቅማቸውም። እነርሱም ይጠፋሉ።

፳፱ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ᵐምክሮች ᵃየሚያደምጡ ከሆነ መማር ጥሩ ነው።

፴ ነገር ግን በዓለም ሀብት ᵐሀብታም ለሆ ኑት ወዮላቸው። ሀብታም በመሆናቸው ᵃድሆችን ይጠላሉና፣ ትሁቶችን ያሳድዳ ሉና፤ ልባቸውም በሀብታቸው ላይ ነውና፤ ስለዚህ፣ ሀብታቸው አምላካቸው ነው። እናም እነሆ፣ ሀብታቸው ደግሞ ከእነርሱ ጋር ይጠፋል።

፴፩ እናም ᵐመስማትን ለማይፈልጉ ለደ ንቆሮዎች ወዮላቸው፤ ይጠፋሉና።

፴፪ ማየትንም ለማይፈልጉ ለዕውሮች ወዮላቸው፤ እነርሱም ደግሞ ይጠፋሉና።

፴፫ ልባቸውን ላልተገረዙት ወዮላቸው፣ የኃጢአታቸው እውቀት በመጨረሻው ቀን ይጎዳቸዋልና።

፴፬ ᵐለውሸታም ወዮለት፣ ወደታች ወደ ᵃሲያል ይጣላልና።

፳፫ ሀ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣ ንስሀ መግባት።
ለ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣ መጥመቅ።
፳፬ ሀ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—የክርስቶስን ስም በራሳችን ላይ መውሰድ።
ለ ቅ.መ.መ. መፅናት።
ሐ ቅ.መ.መ. ኩነኔ።
፳፭ ሀ ያዕ. ፬፡ ፲፯።
ቅ.መ.መ. ህግ።
ለ ሮሜ ፬፡ ፲፭፣ ፪ ኔፊ ፪፡ ፲፫፣ አልማ ፴፪፡ ፲፪–፳፩።
ቅ.መ.መ. መልስ መስጠት፣ ሂሳብ፣ ተጠያቂነት፣ ሀላፊነት።
፳፯ ሀ ሞዛያ ፲፭፡ ፳፬፣ ት. እና ቃ. ፲፴፯፡ ፯።
ለ ሞዛያ ፲፡ ፲፭።
ሐ ፪ ኔፊ ፪፡ ፲፣ አልማ ፴፩፡ ፲፭–፲፯።
ቅ.መ.መ. የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ።
መ ቅ.መ.መ. ፍትህ።
ሠ ዘፍጥ. ፪፡ ፯፣ ት. እና ቃ. ፶፣ ፴፣ አብር. ፭፡ ፯።
፳፯ ሀ ሉቃ. ፲፪፡ ፴፯–፴፰።
፳፰ ሀ አልማ ፳፰፡ ፲፣
ለ ቅ.መ.መ. ከንቱ፣ ከንቱነት።
ሐ ሉቃ. ፲፯፡ ፲፭፣ ፪ ኔፊ ፳፯፡ ፳፣ ፳፰፡ ፡ ፲፭።
መ ምሳ. ፲፡ ፯፣ ኤር. ፰፡ ፰–፱፣ ሮሜ ፭፡ ፳፪።
ቅ.መ.መ. ኩራት፣ ጥበብ።
ሠ አልማ ፴፯፡ ፲፪።
ቅ.መ.መ. ምክር (ስም)።
፳፱ ሀ ያዕቆ. ፡ ፣።
ለ ፪ ኔፊ ፳፰፡ ፳፯።
፴ ሀ ሉቃ. ፲፪፡ ፴፡ ፣ ፩ ጢሞ. ፮፡ ፣ ት. እና ቃ. ፶፯፡ ፲፯።
ለ ቅ.መ.መ. ደሀ።
፴፩ ሀ ሕዝ. ፴፣፡ ፴–፴፣፡ ማቴ. ፲፩፡ ፲፭፣ ሞዛያ ፳፯፡ ፳፰፣ ት. እና ቃ. ፩፡ ፪፣ ፲፩፣ ፲፡ ፣ መሴ ፮፡ ፳፯።
፴፪ ሀ ምሳ. ፣ ፲፱፡ ፱።
ቅ.መ.መ. ሐሰት፣ ታማኝ፣ ታማኝነት።
ለ ቅ.መ.መ. ሲያል።

፴፭ እያወቀ ᵐለሚገድል ለነፍሰ ገዳይ ወዮለት፣ ᵃይሞታልና።

፴፮ ለሚያመነዝሩ ᵐለአመንዝራዎች ወዮ ላቸው፣ ወደታች ወደ ሲኦል ይጣላሉና።

፴፯ አዎን፣ ጣኦትን ᵐለሚያመልኩ ወዮላ ቸው፣ የዲያብሎሶች ሁሉ ዲያብሎስ በእነ ርሱ ይደሰትባቸዋልና።

፴፰ እናም፣ በአጠቃላይ፣ በኃጢአታ ቸው ለሚሞቱ ሁሉ ወዮላቸው፤ ወደ እግ ዚአብሔር ᵐይመለሳሉና፣ እናም ፊቱን ያያሉ፣ በኃጢአታቸውም ይቀራሉ።

፴፱ አቤቱ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ፣ ቅዱስ የሆነውን እግዚአብሔርን መተላለፍ እንዴት መጥፎ እንደሆነ፣ እናም ደግሞ ለዚያ ᵐለተንኮለኛ ፈተናዎች መጋለጥ እን ዴት አስቀያሚ እንደሆነ አስታውሱ። ᵃስለ ዓለም ማሰብ ሞት እንደሆነና፣ ስለመንፈ ሳዊ ነገር ማሰብ ᵐዘለዓለማዊ ᵐህይወት እን ደሆነ አስታውሱ።

፴ አቤቱ፣ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ፣ ቃሌን አድምጡ። የእስራኤሉን ቅዱስ ታላ ቅነት አስታውሱ። እኔ በእናንተ ላይ ከባድ ነገሮችን እንደተናገርኩ አትበሉ፤ ይህንንም ካላችሁ፣ እውነትን ትቃወማላችሁ፤ እኔ የእናንተን ፈጣሪ ቃላት ተናግሬአለሁና። ᵐየእውነት ቃላት ንፁህ ላልሆኑ ሁሉ ላይ ᵃአስቸጋሪ እንደሆነ አውቃለሁ፤ ነገር ግን ጻድቆች አይፈሯቸውም፣ እውነትን ይወ ዳሉና እናም አይጨነቁም።

፴፪ ከዚያም አቤቱ የተወደዳችሁ ወንድ ሞቼ፣ ወደ ጌታ ወደ ቅዱሱ ᵐኑ። መንገዱ ፅድቅ እንደሆነ አስታውሱ። እነሆ፣ ለሰው ᵃመንገዱ ᵐጠባብ ነው፣ ነገር ግን በእርሱ ፊት በቀጥተኛ አቅጣጫ ይጓዛል፣ ᵐመግ ቢያውን ጠባቂ የእስራኤሉ ቅዱስ ነው፤ እናም እርሱ በዚያ ቦታ ምንም አገልጋይ አይቀጥርም፤ እናም በመግቢያው ካልሆነ በቀር ምንም ሌላ መንገድ የለም፤ እርሱ ሊታለል አይችልምና፣ ጌታ አምላክ የእ ርሱ ስም ነውና።

፴፫ እናም ለሚያንኳኳ ሁሉ ለእርሱ ይከፍትለታል፤ እና ᵐብልሆችም፣ የተማ ሩትና፣ ሀብታም ለሆኑት፣ በትምህርታ ቸው፣ በጥበባቸውና በሀብታቸው ኩራት ᵃከፍ ያሉ—አዎን፣ እነርሱን ነው እርሱ የሚጠላው፤ እናም እነዚህን ነገሮች ካል ጣሉም፣ እራሳቸውን በእግዚአብሔር ፊት ᵐሞኞች አድርገው ካላሰቡና፣ ራሳቸውን በጥልቅ ᵐትህትና በጣም ዝቅ ካላደረጉ፣ ለእነርሱ አይከፍትላቸውም።

፴፬ ነገር ግን የብልሆችና የአስተዋዮች ነገሮች—አዎን፣ ለቅዱሳን የተዘጋጀው ያ ደስታ፣ ከእነርሱ ለዘለዓለም ᵐይደበቃሉ።

፴፭ አቤቱ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ቃላቴን አስታውሱ። እነሆ፣ ካባዬን አው ልቄ በፊታችሁ አራግፈዋለሁ፤ የመዳኔ አምላክ ᵐሁሉን በሚያይ ዐይኑ እንዲመለ ከተኝ እፀልያለሁ፤ ስለዚህ፣ ሁሉም ሰዎች እንደስራቸው በሚፈረድባቸው በመጨረ ሻው ቀን፣ የእስራኤል አምላክ ኃጢአታች ሁን ከላዬ ላይ ᵃእንዳወረድኩ፣ እናም በእ ርሱ ፊት በክብር እንደምቆምና ከደማችሁ

፴፭ ᵐ ዘፀአ. ፳፡ ፲፫፤
ሞዛያ ፲፫፡ ፳፭።
ᵃ ቅ.መ.መ. የሞት ቅጣት።
፴፮ ᵐ ፫ ኔፊ ፲፪፡ ፳፯–፳፱።
ቅ.መ.መ. ንጹህነት።
፴፯ ᵐ ቅ.መ.መ. ጣኦት አምላኪ።
፴፰ ᵐ አልማ ፴፡ ፲፭፣ ፲፫።
፴፱ ᵐ ፪ ኔፊ ፳፰፡ ፳–፳፪፤ ፴፪፡ ፳፤
ሞዛያ ፪፡ ፴፪፤ ፬፡ ፲፬፤
አልማ ፴፡ ፶፫።
ᵃ ሮሜ ፳፡ ፮።
ቅ.መ.መ. ስጋዊ።
ሐ ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ሞት።
መ ቅ.መ.መ. የዘለዓለም
ህይወት።
ᵐ ምሳ. ፲፭፡ ፲፱።
፴፱ ᵐ ቅ.መ.መ. እውነት።
ᵃ ፩ ኔፊ ፲፮፡ ፪፣
፪ ኔፊ ፳፰፡ ፳፰፤ ፴፫፡ ፭።
፴፭ ᵐ ፩ ኔፊ ፮፡ ፬፤
ያዕቆ. ፩፡ ፯፤
ኦምኒ ፩፡ ፳፮፤
ሞሮኒ ፣፡ ፴–፴፪።
ᵃ ፪ ኔፊ ፴፩፡ ፲፯–፳፩፤
አልማ ፴፯፡ ፴፯፤
ት. እና ቃ. ፻፴፪፡ ፳፪፣ ፳፭።
ሐ ሉቃ. ፲፫፡ ፳፬፤
፪ ኔፊ ፴፫፡ ፱፤
ሔለ. ፫፡ ፳፱–፴።
መ ፪ ኔፊ ፴፩፡ ፱፣ ፣፯–፣፰፤
፫ ኔፊ ፲፡ ፲፫–፲፬፤
ት. እና ቃ. ፵፫፡ ፯፣
፻፴፯፡ ፪።
፴፪ ᵐ ማቴ. ፲፩፡ ፳፭።
ᵃ ቅ.መ.መ. ኩራት።
ሐ ፩ ቆሮ. ፫፡ ፣፲–፳፩።
መ ቅ.መ.መ. ትሁት፣ ትሕትና።
፴፫ ᵐ ፩ ቆሮ. ፪፡ ፱–፣፲።
፴፬ ᵐ ያዕቆ. ፪፡ ፣።
ᵃ ያዕቆ. ፩፡ ፣፱።

ሓንፁህ እንደሆንኩ እንደሚመሰክር ታው ቃላችሁ።

፻፭ አቤቱ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ፣ ከኃጢአታችሁ ተመለሱ፤ አጥብቆ ከሚ ያስራችሁ የእርሱን ᐸሰንሰለት በጥሱ፤ ወደ መዳናችሁ ᐸዓለት ወደሆነው እግዚአብ ሔር ኑ።

፻፮ ለዚያ ᐸየፍርድ ቀን ለሆነው፣ ᐸፍትህ ለፃድቃን ለሚሰጥበት ለዚያ ለታላቁ ቀን በአሰቃቂ ፍርሃት እንዳትሸማቀቁ፣ ሓኃጢ አታችሁን በፍፁም መልኩ እንዳታስታ ውሱ፣ እናም በታላቅ ድምፅ፡ ቅዱስ ቅዱስ ነው ፍርድህ፣ አቤቱ ᐸሁሉን የሚገዛ ጌታ አምላክ—ነገር ግን ኃጢአቴን አውቃለሁ፤ ህግህን ተላልፌአለሁ፣ መተላለፎቼም የእ ኔው ናቸው፤ እናም ዲያብሎስ እኔን ይዞ ኛል፣ ስለዚህ እኔ የእርሱ ጉዳት የደረሰብኝ የመከራው ተሳዳጅ ነኝ በማለት ለመናገር እንድትገፋፉ ነፍሳችሁን አዘጋጁ።

፻፯ ነገር ግን እነሆ፣ ወንድሞቼ፣ ስለእ ነዚህ መጥፎ ነገሮች እውነታ እንድትነቁ ዘንድ ማድረጌ አስፈላጊ ነውን? አዕምሮ አችሁ ንፁህ ቢሆን ኖሮ እኔ ነፍሶቻችሁን አሰቃይ ነበርን? ከኃጢአታችሁ ንፁህ ብት ሆኑ ኖሮ በእውነቱ ግልፅነት እኔ ለእናንተ ግልፅ እሆን ነበርን?

፻፰ እነሆ፣ ቅዱሳን ብትሆኑ ኖሮ እኔ ስለ ቅዱስነት እነግራችሁ ነበር፤ ነገር ግን እና ንተ ቅዱስ ስላልሆናችሁ፣ እና እኔን እን ደአስተማሪ ስለአያችሁኝ፣ ᐸስለኃጢያት ውጤት ᐸአስተምራችሁ ዘንድ አስፈላጊ ነው።

፻፱ እነሆ፣ ነፍሴ ኃጢያትን ትጠላለች፣ ልቤ ደግሞ በጻድቅነት ትደሰታለች፤ እናም የቅዱስ አምላኬን ስም ᐸአሞግሳለሁ።

፻ ወንድሞቼ ሆይ፣ ኑ፣ የተጠማችሁ ሁሉ፣ ወደ ᐸውኃው ኑ፤ እና ገንዘብ የሌ ላችሁ፣ ኑ ግዙና ብሉ፤ አዎን፣ ኑ ወይንና ወተት ᐸያለገንዘብና ያለዋጋ ግዙ።

፻፩ ስለዚህ፣ ዋጋ በሌለው ነገር ገንዘብ አታባክኑ፣ ወይንም አጥጋቢ ለማይሆን ᐸጉልበታችሁን አታባክኑ፣ እናም አድ ምጡኝ፣ የተናገርኳቸውንም ቃል አስ ታውሱ፤ ወደ እስራኤሉ ቅዱስ ኑ፣ እናም የማይጠፋውን ሊበላሽ የማይቻለውን ᐸተመገቡና፣ ነፍሳችሁ በመፋፋት ትደ ሰት።

፻፪ እነሆ፣ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ፣ የአ ምላካችሁን ቃላት አስታውሱ፤ ያለማቋ ረጥ በቀን ለእርሱ ፀልዩ፣ እናም በመሸ ጊዜ ለቅዱስ ስሙ ᐸምስጋናን አቅርቡ። ልባች ሁም ትደሰት።

፻፫ እናም እነሆ የጌታ ᐸቃል ኪዳን እን ዴት ታላቅ ነው፣ እናም ለሰው ልጆች እራ ሱን ዝቅ ማድረጉ እንዴት ታላቅ ነው፤ በታላቅነቱ፣ በጸጋውና ᐸበምህረቱ የተ ነሳ ለእኛ ዘራችንን በሙሉ በስጋ እንደ ማይጠፋ፣ ነገር ግን እንደሚጠብቃቸው ቃል ገብቶልናል፤ በሚመጡትም ትው ልዶች በእስራኤል ቤት የተቀደሰ ᐸቅርን ጫፍ ይሆናሉ።

፻፬ እናም አሁን፣ ወንድሞቼ ሆይ፣ ለእ ናንተ የበለጠ እናገራለሁ፤ ነገር ግን በማግ ስቱ የተቀሩትን የእኔን ቃላት እገልፅላች ኋለሁ። አሜን።

ምዕራፍ ፲

አይሁድ አምላካቸውን እንደሚሰቅሉ ያዕቆብ ገለጸ—በእርሱም ማመን እስኪ

፻፬ሐ ያዕቆ. ፪፡፪፣
ሞዛያ ፪፡፳፰፡፳፱።
፻፭ ሀ ፪ ኔፊ ፳፰፡፳፱፤
አልማ ፴፯፡፲፰።
ለ ቅ.መ.መ. አለት።
፻፮ ሀ ቅ.መ.መ. ፍርድ፣
የመጨረሻው።
ለ ቅ.መ.መ. ፍትህ።
ሐ ሞዛያ ፫፡፳፭።
መ ፭ ኔፊ ፭፡፲፬፣
ሙሴ ፪፡፭።
፻፰ ሀ ቅ.መ.መ. ኃጢያት።
ለ አልማ ፴፯፡፴፪።
፻፱ ሀ ፭ ኔፊ ፲፰፡፲፯።
፯ ሀ ቅ.መ.መ. ህያው ውሀ።
ለ አልማ ፴፪፡፳፯።
፯፫ ሀ ኢሳ. ፯፭፡፩—፪።
ለ ፪ ኔፊ ፴፩፡፳፣ ፴፪፡፫፣
፫ ኔፊ ፲፪፡፯።
፯፪ ሀ ቅ.መ.መ. አመስጋኝ፣
ምስጋናን፣ ምስጋና
መስጠት።
፯፫ ሀ ቅ.መ.መ. ቃል ኪዳን።
ለ ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።
ሐ ቅ.መ.መ. የጌታ የወይን
አትክልት ስፍራ።

ጀምሩም ድረስ ይበተናሉ—አሜሪካ ንጉስ የማይገዛባት የነፃ ምድር ትሆናለች— ራሳ ችሁን ከእግዚአብሔር ጋር አስታርቁ፣ እናም በፀጋው መዳንን አግኙ። ፳፻፶፬–፳፻፶፯ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም አሁን የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፣ እኔ ያዕቆብ ስለዚህ ስለተናገርኩት ስለተቀደሰው ᵐቅርንጫፍ ደግሜ እናገራ ችኋለሁ።

፪ እነሆም እኛ የያዝናቸው ᵐቃልኪዳኖች ለስጋ የተገቡ ቃልኪዳኖች ናቸው፤ ስለ ዚህ፣ ብዙዎች ልጆቻችን እምነት በማ ጣታቸው የተነሳ እንደሚጠፉ ለእኔ ቢገ ለፀልኝም፣ ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር ለብዙዎች ምህረትን ያወርዳል፤ እና ልጆ ቻችን የመድኃኒታቸውን እውነተኛ እው ቀት ወደሚሰጣቸው ለመምጣት ደግመው ይመለሳሉ።

፫ ስለዚህ፣ እንዳልኳችሁ፣ ክርስቶስ— ትናንት ማታ ᵐመልእኩ ስሙ ይህ እንደ ሚሆን ነግሮኛልና—ከአይሁዶች፣ በዓ ለም ከሌሎች በላይ ኃጢአተኛ በሆኑት፣ መካከል ᵃይመጣል፤ እነርሱም ᵐይሰቅሉ ታል—እንዲህ መሆኑ ለአምላካችን አስ ፈላጊ ነበርና፣ እናም በምድር ላይ የራ ሳቸውን ᵐአምላክ ᵐየሚሰቅል ሌላ ህዝብ የለም።

፬ በሌሎች ሕዝቦች መካከል ታላቅ ᵐተዓ ምራት ከተፈፀሙ ንስሀ ይገባሉ፣ እናም አምላካቸው እንደሆነ ያውቃሉ።

፭ ነገር ግን በኃጢያትና ᵐበካህናት ተንኮል የተነሳ በኢየሩሳሌም ያሉት እርሱ እስኪገ ደል ድረስ እንኳ በእርሱ ላይ አንገተ ደን ዳና ይሆናሉ።

፮ ስለዚህ በኃጢአታቸው የተነሳ ጥፋት፣ ረሃብ፣ ቸነፈር፣ እና ደም መፍሰስ በእነርሱ ላይ ይመጣል፤ እናም የማይጠፉት ደግሞ በህዝቦች ሁሉ መካከል ᵐይበተናሉ።

፯ ነገር ግን እነሆ፣ ᵐጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል—እኔ ክርስቶስ እንደሆንኩ፣ የሚያምኑበት ቀን ᵃበመጣ ጊዜ፣ ያኔ እኔ በስጋ ወደ ርስታቸው ምድር እመልሳቸው ዘንድ ከአባቶቻቸው ጋር ቃል ኪዳን ገብቻ ለሁ።

፰ እናም እንዲህ ይሆናል፣ ከረጅም ዘመን ብተናቸው፣ ᵐከባህር ደሴቶችና፣ ከምድር ከአራቱም ማዕዘናት ᵃይሰበሰባሉ፤ እና አህዛቦች እነርሱን ወደ ርስት ምድራቸው ᵐበመውሰዳቸው የአህዛብ ሀገሮች በዐይኖቼ ፊት ታላቅ ይሆናሉ ይላል እግዚአብሔር።

፱ ᵐአዎን፣ የአህዛብ ንጉሶች ለእነርሱ እንደ አባት ይሆኑላቸዋል፣ እናም ንግስ ቶቻቸውም እንደ እናቶች ይሆኑላቸዋል፤ ስለዚህ፣ ጌታ ለአህዛብ የገባው ᵃቃል ኪዳን ታላቅ ነው፣ እርሱ ተናግሯታልና፣ እናም ማን ይቃወማል?

፲ ነገር ግን እነሆ፣ ይህ ምድር፣ ይላል እግዚአብሔር፣ የርስታችሁ ምድር ይሆ ናል፣ እና ᵐአህዛብም በምድሩ ላይ የተባ ረኩ ይሆናሉ።

፲፩ እናም ይህ ምድር ለአህዛብ ᵐየነፃነት ምድር ይሆናል፣ እናም በምድሪቷም በአ ህዛብ ላይ የሚነሱ ᵃንጉሶች አይኖሩም።

፲ ፩ ᵐ ፩ ኔፊ ፲፭፡ ፲፪–፲፯፤
፪ ኔፊ ፫፡ ፭፤
ያዕቆ. ፭፡ ፶፫–፶፭።
፪ ᵐ ፩ ኔፊ ፳፪፡ ፳፣
፫ ኔፊ ፭፡ ፳፭–፳፯፤
፳፩፡ ፱–፲፯።
፫ ᵐ ፪ ኔፊ ፳፭፡ ፲፱፤
ያዕቆ. ፯፡ ፭፤
ሞሮኒ ፯፡ ፳፪።
ᵃ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ
ክርስቶስ—ስለኢየሱስ
ክርስቶስ መወለድ እና ሞት
ትንቢቶች።
ሐ ፩ ኔፊ ፲፩፡ ፴፫፤
ሞዛያ ፫፡ ፱፤
ት. እና ቃ. ፶፭፡ ፶፪–፶፫።
መ ፩ ኔፊ ፲፱፡ ፲።
ሠ ሉቃ. ፳፫፡ ፳–፳፱።
፩ ᵐ ቅ.መ.መ. ተአምራት።
፭ ᵐ ሉቃ. ፳፪፡ ፪።
ቅ.መ.መ. የካህን ተንኮል።
፮ ᵐ ፩ ኔፊ ፲፱፡ ፲፣–፲፱።
ቅ.መ.መ. እስራኤል—
የተበተኑት እስራኤል።
፯ ᵐ ቅ.መ.መ. ጌታ።
ᵃ ፪ ኔፊ ፳፭፡ ፲፣–፲፯።
፰ ᵐ ፩ ኔፊ ፳፪፡ ፱፤
፪ ኔፊ ፲፡ ፳–፳፪፤
ት. እና ቃ. ፱፴፫፡ ፳።
ᵃ ቅ.መ.መ. እስራኤል—
የእስራኤል መሰብሰብ።
ሐ ፩ ኔፊ ፳፪፡ ፳።
፱ ᵐ ኢሳ. ፶፱፡ ፳፪–፳፫።
ᵃ ፩ ኔፊ ፳፪፡ ፳–፱፤
ት. እና ቃ. ፫፡ ፲፱–፳።
፲ ᵐ ፪ ኔፊ ፯፡ ፲፪።
፲፩ ᵐ ቅ.መ.መ. ነጻ፣ ነጻነት።
ᵃ ሞዛያ ፳፱፡ ፴፩–፴፪።

፲፪ እናም እኔ ይህንን ምድር ከሌሎች ሀገሮች አጠናክራቸዋለሁ።

፲፫ እናም ፅዮንን ᵐየሚዋጋ ᵃይጠፋል፣ ይላል እግዚአብሔር።

፲፬ በእኔ ላይ ሌላ ንጉስ የሚያስነሳ ይጠፋ ልና፣ ምክንያቱም እኔ ጌታ የሰማይ ᵐንጉስ፣ ንጉሳቸው እሆንላቸዋለሁ፣ እናም ድምፄን ለሚሰሙ ሁሉ ለዘለዓለም ᵃብርሃን እሆን ላቸዋለሁ።

፲፭ ስለዚህ፣ በዚህ የተነሳ፣ ለሰው ልጆች የገባኋቸው ᵐቃልኪዳኖች ይፈፀሙ ዘንድ፣ እነርሱ በስጋ እያሉ አደርግላቸው ዘንድ፣ ᵃየጭለማ ᵐየሚስጥር ስራዎችንና፣ ግድያ ዎችን፣ እናም እርኩሰቶችን አጠፋ ዘንድ ያስፈልገኛል።

፲፮ ስለዚህ፣ አይሁድም ሆነ አህዛብ፣ ባር ያም ሆነ ነፃ፣ ወንድም ሆነ ሴት፣ ᵐፅዮንን የሚዋጋ ይጠፋል፤ የምድር ሁሉ ጋለሞ ታዎች ᵃእነዚህ ናቸውና፤ የእኔ ᵐያልሆኑት ᵐይቃወሙኛልና ይላል አምላካችን።

፲፯ ለሰው ልጆች በስጋቸው ላደርግላቸው የገባሁትን ቃል ኪዳን ᵐእፈፅማለሁና—

፲፰ ስለዚህ፣ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፣ አምላካችን እንዲህ ይላል፣ ዘሮቻ ችሁን ᵐበአህዛብ እጅ አሰቃያለሁ፣ ይሁን እንጂ፣ እነርሱ እንደአባት ይሆኑላቸው ዘንድ የአህዛብን ልብ አራራለሁ፤ ስለዚህ፣ አህዛብ ᵃይባረካሉ እናም ከእስራኤል ቤትም ውስጥ ᵐይቆጠራሉ።

፲፱ ስለዚህ፣ ለዘሮችህና ከዘሮችህ መሀል ለሚቆጠሩት ይህችን ምድር የርስት ምድ ራቸው ለዘለዓለም ትሆን ዘንድ ᵐእቀባታ ለሁ፤ እግዚአብሔርም ለእኔ ከሌሎች ምድ ሮች ሁሉ በላይ የተመረጠች ምድር ናት አለኝ፤ ስለዚህ፣ በዚያ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ እኔን እንዲያመልኩ እፈልጋለሁ ይላል እግ ዚአብሔር።

፳ እና አሁን፣ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፣ መሀሪው እግዚአብሔር እነዚህን ነገ ሮች በተመለከተ ታላቅ እውቀትን ስለሰ ጠን፣ እናስታውሰው፣ እናም ኃጢአታ ችንን እንተው፣ ተስፋም አንቁረጥ፣ እኛ አልተጣልንምና፤ ይሁን እንጂ፣ ከርስታ ችን ምድር ᵐእንድንወጣ ተደርገናል፤ ነገር ግን ᵃወደተሻለ ምድር ተመርተናል፣ ጌታ ባህሩን ᵐመንገዳችን አድርጎልናል፣ እና ᵐበባህር ደሴት ላይ ነን።

፳፩ ነገር ግን ᵐበባህር ደሴቶች ላይ ላሉት የጌታ ቃል ኪዳን ታላቅ ነው፣ ስለዚህ ደሴ ቶች ስለሚል፣ ከዚህ የበለጡ ሌሎችም አሉ ማለት ነው፤ እናም እነርሱ ወንድሞቻችን የሚኖሩባቸው ናቸው።

፳፪ እነሆም ጌታ እግዚአብሔር እንደፈቃ ዱና እንደምኞቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ ከእስራ ኤል ቤት ህዝቡን ᵐአውጥቷል። እናም አሁን እነሆ፣ ጌታ የተገነጠሉትን ሁሉ ያስታው ሳል፣ ስለዚህ እኛንም ደግሞ ያስታውሳል።

፳፫ ስለዚህ፣ ልባችሁን አስደስቱ፣ እናም በራሳችሁ ᵐለመስራት፣ ዘለዓለማዊውን ሞት ወይም የዘለዓለማዊውን ህይወት መን ገድ እራሳችሁ ᵃለመምረጥ ᵐነጻነት እንዳላ ችሁ አስታውሱ።

፲፫ ሀ ፩ ኔፊ ፳፪፡፲፡ ፲፱።
ለ ኢሳ. ፰፡፲፪።
፲፬ ሀ አልማ ፭፡፶፣
ት. እና ቃ. ፴፰፡፳፭–፳፪፣
፲፳፰፡፳፪–፳፫፣
ሙሴ ፯፡፶፣
ለ ቅ.መ.መ. ብርሀን፣ የክርስቶስ ብርሀን።
፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. ቃል ኪዳን።
ለ ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ጭለማ።
ሐ ሔለ. ፫፡፳፫።
ቅ.መ.መ. የሚስጥር ስብሰባ።
፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. ፅዮን።
ለ ፩ ኔፊ ፲፫፡፴–፳።
ሐ ፩ ኔፊ ፲፡፡፣ ፩ ኔፊ
፳፪፡፲፫–፳፫፣
፪ ኔፊ ፳፡፡–፲፭–፴፪፣
፫ ኔፊ ፲፯፡፡–፲፭፣
ኤተር ፪፡፱።
መ ማቴ. ፲፪፡፴።
፲፯ ሀ ት. እና ቃ. ፩፡፴፡፡
፲፡ ሀ ሉቃ. ፲፡፳፡–፴፡
ት. እና ቃ. ፴፭፡፯–፴።
ለ ኤፌ. ፫፡፯።
ሐ ገላ. ፫፡፯፣ ፳፱፣
፩ ኔፊ ፲፡፡፡–፪፣
፫ ኔፊ ፲፯፡፲፣ ፳፩፡፯፣
፳፪፣ ፴፡፪፣
አብር. ፪፡፱–፲፩።
፲፱ ሀ ፪ ኔፊ ፫፡፪።
፳ ሀ ፩ ኔፊ ፪፡፩–፡።
ለ ፩ ኔፊ ፪፡፳።
ቅ.መ.መ. የቃል ኪዳን ምድር።
ሐ ፩ ኔፊ ፲፡፡–፫፣
መ ኢሳ. ፲፩፡፣ ፣–፲፪።
፳፩ ሀ ፩ ኔፊ ፲፱፡፲፫–፲፯፣ ፳፪፡፡።
፳፪ ሀ ፩ ኔፊ ፳፪፡፡።
፳፫ ሀ ፪ ኔፊ ፪፡፣–፡።
ለ ፩ ኔፊ ፪፡፳።
ቅ.መ.መ. ነጻ ምርጫ።

፳፬ ስለዚህ፣ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፣ ራሳችሁን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር እንጂ ከዲያብሎስና ከስጋ ፈቃድ ጋር አታስታርቁ፤ እናም ከእግዚአብሔር ጋር ከታረቃችሁ በኋላ [ሀ]የምትድኑት በእግዚአብሔር [ለ]ፀጋ ውስጥና በእርሱ በኩል ብቻ እንደሆነ አስታውሱ።

፳፭ ስለዚህ፣ ወደዘለዓለም የእግዚአብሔር መንግስት እንድትገቡና፣ በመለኮታዊ ፀጋም እንድታመሰግኑት ዘንድ፣ እግዚአብሔር በትንሣኤ ኃይል ከሞት፣ እናም ደግሞ ከዘለዓለማዊው ሞት [ሐ]በኃጢያት ክፍያ ያንሳችሁ። አሜን።

ምዕራፍ ፲፭

ያዕቆብ መድኃኒቱን አየ—የሙሴ ህግ የክርስቶስ ምሳሌዎች ናቸው እናም የእርሱን መምጣት ያረጋግጣል። ከ፳፻፶፬–፳፻፶፮ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም አሁን፣ [ሀ]ያዕቆብ በዚያን ጊዜ ለህዝቤ ብዙ ነገሮችን ተናገረ፤ ሆኖም እነዚህን ነገሮች ብቻ [ለ]እንዲፃፉ አደረግሁ፣ ምክንያቱም እኔ የፃፍኳቸው ነገሮች ይበቁኛልና።

፪ እናም አሁን እኔ ኔፊ፣ [ሀ]የኢሳይያስን ቃል በተጨማሪ እፅፋለሁ፣ ምክንያቱም በእርሱ ቃል ነፍሴ ትደሰታለች። ቃላቱን ለህዝቤ አመሳስልላቸዋለሁ፣ እናም ለልጆቼ ሁሉ አሰራጫቸዋለሁ፣ ምክንያቱም እርሱ በእውነት [ለ]መድኃኒቴን፣ እኔ እንዳ የሁት፣ አይቶታልና።

፫ እናም እኔ እንዳየሁት ወንድሜ ያዕቆብም ደግሞ [ሀ]አይቶታል፤ ስለዚህ፣ ቃሌ እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ የእነርሱን ቃል ለልጆቼ እልካለሁ። ስለዚህ፣ እግዚአብሔር [ለ]በሶስት ሰዎች ቃል ቃሌን አፀናለሁ ብሏል። ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር የበለጡ ምስክሮችን ይልካል፣ እናም ቃሉን በሙሉ ያረጋግጣል።

፬ እነሆ፣ [ሀ]የሚመጣውን ክርስቶስ እውነታ ለህዝቦቼ [ለ]በማረጋገጥ ነፍሴ ትደሰታለች፤ ለዚህም ምክንያት ነው የሙሴ [ሐ]ህግ የተሰጠው፤ እናም ከዓለም መጀመሪያ ጀምሮ ለሰዎች በእግዚአብሔር የተሰጡት ነገሮች ሁሉ የእርሱ ምሳሌዎች ናቸው።

፭ እናም ደግሞ ነፍሴ ጌታ ለአባቶቻችን በገባው [ሀ]ቃል ኪዳን ትደሰታለች፤ አዎን፣ በፀጋውና በፍርዱና፤ በሀይሉ እና በምህረቱ፣ በታላቁና ከሞት በሚያድነው ዘለአለማዊው እቅዱ፣ ነፍሴ ትደሰታለች።

፮ እናም ክርስቶስ ካልመጣ [ሀ]በስተቀር ሁሉም ሰው እንደሚጠፋ ለህዝቤ በማረጋገጤ ነፍሴ ትደሰታለች።

፯ ክርስቶስ [ሀ]ከሌለ እግዚአብሔር አይኖርምና፤ እናም እግዚአብሔር ከሌለ እኛም አንኖርም፣ ምክንያቱም ምንም ፍጡር [ለ]ሊኖር አይችልምና። ነገር ግን እግዚአብሔር አለ፣ እርሱም ክርስቶስ ነው፣ እናም በዘመኑ ፍፃሜ ይመጣል።

፰ እናም አሁን ከህዝቤ ማንም ይህንን ቃል የሚያይ ልብን ከፍ እንዲያደርጉና ለሰዎች ሁሉ ይደሰቱ ዘንድ፣ ከኢሳይያስ ቃል በጥቂቱ እፅፋለሁ። አሁን ቃሉ ይህ ነው፣ እናም በራሳችሁና በሁሉም ሰዎች አነፃፅሯቸው።

ምዕራፍ ፲፮

ኢሳይያስ የኋለኛውን ቀን ቤተመቅ

፳፬ ሀ ቅ.መ.መ. ደህንነት።
ለ ቅ.መ.መ. ጸጋ።
፳፭ ሀ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ።
፲፭ ፩ ሀ ፪ ኔፊ ፮፡ ፩–፲።
ለ ፪ ኔፊ ፴፩፡ ፩።
፪ ሀ ፲ ኔፊ ፳፲፡ ፩።
ለ ቅ.መ.መ. መድኃኒት።
፲ ሀ ፪ ኔፊ ፪፡ ፲፡ ያዕቆ. ፯፡ ፭።
ለ ፪ ኔፊ ፳፯፡ ፲፪፣ ኤተር ፭፡ ፪–፩፣ ት.እና ቃ. ፭፡ ፲፩።
፩ ሀ ያዕቆ. ፩፡ ፭፣ ጀረም ፩፡ ፲፩፣ አልማ ፳፭፡ ፲፩–፲፯፣ ኤተር ፲፪፡ ፲፱።
ለ ፪ ኔፊ ፴፩፡ ፪።
ሐ ፪ ኔፊ ፭፡ ፲።
፭ ሀ ቅ.መ.መ. የአብርሐም ቃል ኪዳን።
፯ ሀ ሞዛያ ፲፡ ፲፩።
፯ ሀ ፪ ኔፊ ፪፡ ፲፣ ።
ለ ቅ.መ.መ. መፍጠር፣ ፍጥረት።

ደስ፤ የእስራኤልን መሰብሰብና የአንድ ሺህ ዘመን ፍርድን እና ሰላምን ተመለ ከተ—በዳግም ምፅአቱ ኩራተኞችና ኃጢ አተኞች ትሁት ይሆናሉ—ኢሳይያስ ፪ አነጻፅሩ። ከ፳፪፡፱–፳፭ ም.ዓ. ገደማ።

፩ የአሞጽ ልጅ [ሀ]ኢሳይያስ ስለ ይሁዳና ስለ ኢየሩሳሌም [ለ]ያየው ቃል—

፪ እናም በኋለኛው ቀናት እንዲህ ይሆ ናል፣ የጌታ [ሐ]ቤት [ተ]ተራራ በተራሮች ጫፍ ላይ ሲመሰረት፣ እናም [ሐ]ከኮረብቶችም በላይ ከፍ ሲል፣ ህዝቦችም ሁሉ ወደ እርሱ ይሰበሰባሉ።

፫ ከእዚያም ብዙ ህዝብ ሄደው እንዲህ ይላል፣ ኑና ወደ ጌታ ተራራ ወደ ያዕቆብ አምላክ ቤት እንውጣ፤ እናም እርሱ መን ገዱን ያስተምረናልና፣ በጎዳናው [ሀ]እንራመ ዳለን፣ [ለ]ህግ ከፅዮን፣ የጌታም ቃል ከኢየ ሩሳሌም ይወጣልና።

፬ እናም እርሱ በሃገሮች መካከል [ሀ]ይፈ ርዳል፣ ብዙ ህዝቦችንም ይገስፃል፣ እናም ሰይፋቸውን ማረሻ፣ ጦራቸውንም ማጭድ ለማድረግ ይቀጠቅጣሉ—ሀገርም በሃገር ላይ ሰይፍ አያነሳም፣ ጦርነትም ከእንግ ዲህ ወዲህ አይማሩም።

፭ የያዕቆብ ቤት ሆይ፣ ኑ በጌታ ብርሃን እንራመድ፤ አዎን፣ ኑ ሁላችሁም [ሀ]ተቅ በዝብዛችኋልና፣ እያንዳንዱም በኃጢያት ወደገዛ መንገዱ አዘነበለ።

፮ ስለዚህ፣ አቤቱ ጌታ፣ ሕዝብህን የያዕ ቆብን ቤት ትተሃል፣ ምክንያቱም እነርሱ የምስራቅን ሰዎች ልምድ [ሀ]ስለተሞሉና፣ እንደ [ለ]ፍልስጤማውያን ምዋርተኞችን ስለ ሚያዳምጡ፣ እና በባዕድ ልጆች [ሐ]እራሳቸ ውን ስላስደሰቱ ነው።

፯ ምድራቸውም ደግሞ በብርና በወርቅ ተሞልታለች፣ ለመዛግብቶቻቸውም ፍጻሜ የለውም፤ ምድራቸውም ደግሞ በፈረሶች ተሞልታለች፣ ሰረገሎቻቸውም ፍፃሜ የላ ቸውም።

፰ ምድራቸውም ደግሞ [ሀ]በጣዖት ተሞል ታለች፤ በጣቶቻቸውም ለሰሩት ለእጃቸው ስራ ይሰግዳሉ።

፱ እናም ተራው ሰው [ሀ]አልሰገደም፣ እናም ታላቁም ሰው እራሱን ትሁት አላደረገም፣ ስለዚህ፣ ይቅር አትበለው።

፲ እናንተ ክፉዎች ሆይ ወደ ድንጋዩ ዋሻ ግቡ፣ እናም በመሬት ውስጥም [ሀ]ተሸሸጉ፣ ምክንያቱም የጌታ ፍርሃትና የክብሩ ሞገስ ክብሩ ይመታችኋል።

፲፩ እናም እንዲህ ሆነ ኩራት የሆነው የሰው አመለካከት አልባሌ ይሆናል፣ የሰ ዎችም ትዕቢት ዝቅ ትላለች፣ እናም ጌታ ብቻውን በዚያ ቀን ከፍ ከፍ ይላል።

፲፪ የሰራዊት ጌታ [ሀ]ቀን በሁሉም ሀገር ላይ፣ አዎን፣ በማንኛውም ላይ፣ አዎን፣ [ለ]በትዕቢተኛውና በኩራተኛው ላይና፣ ከፍ ባለውም ላይ ሁሉ በቅርቡ ይመጣልና፣ እናም እርሱም ይዋረዳል።

፲፫ አዎን፣ እናም የጌታ ቀን በሊባኖስ

፲፪ ፩ *ሀ* ኢስይያስ ምዕራፍ ፪–፲፩ ከነህስ ሰሌዳዎች ውስጥ በ፪ ኔፊ ፲፪–፲፡ ውስጥ ኔፊ ተጠቅሰዋል፤ መጠቆም ያለባቸው አንዳንድ ልዩነቶች አሉ።

ለ ዕብ. *ከሃዛሀ*፣ ይህም “አስቀድሞ መመልከት” ማለት ነው። ይህም ኢሳይያስ ይህን መልእክቱን የተቀበለው በጌታ ራዕይ በኩል ነው ማለት ነው።

፪ *ሀ* ቅ.መ.መ. ቤተመቅደስ፣ የጌታ ቤት።

ለ ኢዩ. ፫፡ ፣ ፲፯።

ቅ.መ.መ. ፅዮን።

ሐ ት. እና ቃ. ፶፱፡ ፷፭።

፫ *ሀ* ቅ.መ.መ. መራመድ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መራመድ (መሄድ)።

ለ ዕብ. ትምህርት። ቅ.መ.መ. ወንጌል።

፩ *ሀ* ፪ ኔፊ ፳፭፡ ፪–፱።

፭ *ሀ* ፪ ኔፊ ፳፯፡ ፲፡ ፣ ሞዛያ ፲፡ ፡ ፤ አልማ ፭፡ ፴፯።

፮ *ሀ* ይህም ተሞልተዋል፣ ትምህርቶች ተሰጥቷቸዋል፣ ከውጪ የመጡ እምነቶች ማለት ነው።

መዝ. ፻፯፡ ፴፭።

ለ ቅ.መ.መ. ፍልስጤማውያን።

ሐ ዕብ. እጅን በ. . .መምታት፣ ወይም ከ. . .ጋር ቃል ኪዳን መግባት።

፰ *ሀ* ቅ.መ.መ. ጣኦት አምላኪ።

፱ *ሀ* ይህም ወደ እግዚአብሔር፤ በምትክ ጣዖቶችን አመለከ ማለት ነው።

፲ *ሀ* አልማ ፲፪፡ ፲፡።

፲፪ *ሀ* ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።

ለ ሚል. ፡ ፣ ፤ ፪ ኔፊ ፳፫፡ ፣ ፲፭፣ ት. እና ቃ. ፳፡ ፣ ፳፭።

ዝግባዎች ላይ ሁሉ ይመጣል፣ ምክንያ
ቱም እነርሱ ከፍና ኮራ ብለዋልና፤ እናም
በበሳንም ዛፍ ሁሉ ላይ፤
፲፡ እናም ከፍ ባሉት ተራሮች ላይ ሁሉ፣
እናም በኮረብታዎች ላይ ሁሉ፣ እና በኮ
ሩት ሀገሮች ሁሉ ላይ፣ እናም በማንኛውም
ሀገር ላይ፤
፲፩ እናም በማንኛውም ረጅም ግንብና፣
በተመሸገውም ቅጥር ላይ ይመጣል፤
፲፪ እናም [ሀ]በባህሩ መርከቦች ላይ ሁሉና፣
በተርሴስ መርከብ ላይ ሁሉ፣ እናም አስደ
ሳች ምስሎች ላይ ሁሉ።
፲፫ እናም የሰው የኩራት አመለካከት
ይወድቃልና፣ የሰዎች ዕብሪትም ይዋረ
ዳል፤ እናም [ሀ]በዚያም ቀን ጌታ ብቻውን
ከፍ ከፍ ይላል።
፲፡ እናም ጣዖቶችን ፈፅሞ ያጠፋል።
፲፡ እናም እነርሱ ጌታ ምድርን በከፍ
ተኛ ሁኔታ ያናውጥ ዘንድ በተነሣ ጊዜ ወደ
ድንጋይ ጉድጓዶችና፣ ወደ ምድር ዋሻዎች
ይገባሉ፣ የጌታ ፍርሃት ይመጣባቸዋልና፣
እናም የእርሱ ግርማ ሞገሱ ክብር ይመታ
ቸዋልና።
፲፡ በዚያም ቀን ሰው ይሰግድላቸው ዘንድ
ያበጃቸውን የብር ጣዖቶቹን፣ እና የወር
ቁን ጣዖቶቹን ለፍልፈልና ለሌሊት ወፍ
[ሀ]ይጥላል፣
፲፡፩ ጌታ ምድርን በከፍተኛ ሁኔታ ያና
ውጥ ዘንድ በተነሳ ጊዜ፣ የጌታ ፍርሃት
ስለሚመጣባቸው፣ እናም የእርሱ ግርማ
ሞገሱ ክብር ስለሚመታቸው ወደ ተሰነ
ጣጠቁ የድንጋይ ዋሻና ወደ ፍርስራሽ ዓለ
ቶች ጫፍ ይገባሉ።
፲፡፪ እስትንፋሱ በአፍንጫው ያለበትን
ሰው [ሀ]ተዉት፣ እርሱ ስለ ምን ይቈጠራል?

ምዕራፍ ፲፫

*ይሁዳና ኢየሩሳሌም ባለመታዘዛቸው ይቀ
ጣሉ—ጌታም ለህዝቡ ይማፀናል፣ እናም
ሕዝቡን ይፈርዳል—የፅዮን ሴት ልጆች
በዓለማዊነታቸው የተነሳ የተረገሙና የተ
ሰቃዩ ናቸው—ኢሳይያስ ፫ን አነጻፅሩ።
ከ፳፪፡፳፪–፳፫፡፳፯ ም.ዓ. ገደማ።*

፩ እነሆም፣ የሰራዊት ጌታ እግዚአብ
ሔር፣ ከኢየሩሳሌምና ከይሁዳ፣ ምርኩ
ዝን፣ እና ድጋፍን፣ የዳቦን ድጋፍ ሁሉ
እናም የውሃንም ድጋፍ ሁሉ ይወስዳል—
፪ ሀያሉን ሰውና፣ ተዋጊውንም፣ ፈራጁ
ንም፣ ነቢዩንም፣ ብልሁንና፣ ሽማግሌውን
ሰው ይወስዳል፤
፫ የሀምሳ አለቃውንና፣ የተከበረውን
ሰው፣ አማካሪውንም፣ እና ብልሁን ሠራ
ተኛና፣ ጥሩ ተናጋሪውን ይወስዳል።
፬ እናም ልጁሎቻቸው ይሆኑ ዘንድ ሕፃ
ናትን እሰጣቸዋለሁ፣ ሕፃናቶችም እነር
ሱን ይገዛሉ።
፭ እናም ሕዝቡ ይጨቆናል፣ አንዱ በሌለ
ኛው፣ እንዲሁም አንዱ በጎረቤቱ፤ ሕፃናቱ
በሽማግሌው ላይ እንዲሁም ፀያፍ አድራጊ
ዎች በተከበረው ላይ ይኮራሉ።
፮ አንድ ሰው በአባቱ ቤት ውስጥ ወንድ
ሙን በያዘ ጊዜ፣ እናም እንዲህ ሲለው፥
አንተ ልብስ አለህ፣ አለቃም ሁንልን፣
እናም ይህም [ሀ]ጥፋት ከእጅህ በታች እን
ዲሆን አትፍቀድ—
፯ በዚያ ቀን እንዲህ በማለት ይም
ላል—[ሀ]ባለመድሀኒት አልሆንም፤ ምክንያ
ቱም በቤቴ ዳቦም ሆነ ልብስ የለምና፤ የሕ
ዝቡም አለቃ አታድርጉኝ።
፰ የክብሩን ዐይን ለማስቆጣት፣ ምላሳ

፲፯ *ሀ* የግሪክ (ሰፕቱአግኒት) መፅሐፍ የእብራውያን መፅሐፍ የሌለው አንዳንድ ቃላት አለው፣ እናም የእብራውያንመፅሐፍ የግሪክ መፅሐፍ የሌለው አንዳንድ ቃላት አለው፤ ነገር ግን ፪ ኔፊ ፲፪፡ ፲፯ ሁለቱም አለው።

መዝ. ፴፰፡ ፯፤ ሕዝ. ፳፯፡ ፳፭።

፲፯ *ሀ* ይህም በጌታ በክብር የሚመ ጣበት ቀን ማለት ነው።

፳ *ሀ* ዕብ. መጣል።

፳፪ *ሀ* ይህም በስጋዊ ሰው መመካትን አቁም፤ እግዚአብሔር ካለው ሀይል ሲነጻጸር ትንሽ ነው ማለት ነው።

ሙሴ ፩፡ ፲።

፲፫ ፮ *ሀ* ኢሳ. ፫፡ ፮።

፮ *ሀ* ዕብ. የሚያስር (ቁስልን)፤ ይህም ለችግርህ መፍትሄ ልሰጥህ አልችልም ማለት ነው።

ቸውና ስራቸው ጌታን ስለሚፃረሩ ኢየሩ
ሳሌም ᵐፈረሰች፣ እናም ይሁዳ ᵃወደቀች።
፳ በፊታቸው የሚታየው በእነርሱ ላይ
ይመሰክራል፣ እናም ኃጢአታቸው ᵐእንደሰ
ዶም አይነት እንደሆነ ያውጃል፣ እናም ሊደ
ብቁት አይችሉም። በራሳቸው ላይ ኃጢያ
ትን በማምጣታቸው ለነፍሳቸው ወዮላቸው!
፲ የስራቸውን ፍሬ ይበላሉና፤ ፃድቃንን
ᵐመልካም ይሆንላችኋል በላቸው።
፲፩ ወዮላቸው ለክፉዎች፤ ይጠፋሉና፤
የስራቸውም ዋጋ በእነርሱ ላይ ይሆናል!
፲፪ እናም ሕዝቤ፣ ሕፃናት ጨቋኞቸው
ናቸው፣ እንዲሁም ሴቶች ገዢዎቻቸው
ናቸው። ሕዝቤ ሆይ፣ ᵐየመሩአችሁ ያስ
ቱአችኋል፣ እንዲሁም የምትሄዱበትንም
መንገዳችሁን ያጠፋሉ።
፲፫ ጌታ ᵐለሙግት ተነስቷል፣ እናም በሕ
ዝቡም ላይ ሊፈርድ ቆሟል።
፲፬ ጌታ ከሕዝቡ ሽማግሌዎችና ᵐከልዑ
ሎች ጋር ለፍርድ ይገባል፤ ምክንያቱም
ᵃየወይኑን ቦታ እና በቤታችሁ የሚገኙት
ሐድሆችን ᵐብዝበዛ ᵐየጨረሳችሁ እናንተ
ናችሁ።
፲፭ እናንት ምን ማለታችሁ ነው? ሕዝ
ቤን ታደቁአቸዋላችሁ፣ እና የድሆችንም
ፊት ትፈጫላችሁ፣ ይላል የሰራዊት ጌታ
እግዚአብሔር።
፲፮ ከሁሉም በላይ፣ ጌታ እንዲህ አለ፥
የፅዮን ሴት ልጆች ትዕቢተኛ ስለሆኑና
አንገታቸውን በማስገግ ስለሚራመዱና
በሚሄዱበት ጊዜ ዐይናቸውን በማጣቀስ፣
ᵐፈጠን ብለው በመራመድ እናም በእግራ
ቸው እያቃጨሉ በመሄዳቸው ምክንያት—
፲፯ ስለዚህ ጌታ የፅዮንን ሴት ልጆች ራስ
በቡሃነት ይመታል፣ እናም ጌታ ᵐሀፍረተ-
ስጋቸውን ይገልጣል።
፲፰ በዚያ ቀን ጌታ የሚያንቃጭለውን
ጌጣቸውን፣ ᵐመርበብን፣ እና ጨረቃ የሚ
መስለውን ᵃየአንገት ጌጣቸውን ውበት ያስ
ወግዳል።
፲፱ ሰንሰለቱንና አምባሩን፣ እና ᵐመሸፈ
ኛውን፤
፳ ቆብና የእግር አልቦውን፣ እና የራስ
ማሰሪያውንና፣ የሽቶውን ዕቃ፣ እና የጆሮ
ቀለበቶቹን፤
፳፩ ቀለበት እና የአፍንጫ ጌጥ፤
፳፪ ᵐውድ ሱፍ ልብስንም፣ ካባውንንም፣
መጎናፀፊያውንም፣ እና ፀጉር መጠቅለያ
ውን፤
፳፫ ᵐመስታወቱንም፣ ከጥሩ በፍታ የተሰ
ራውንም ልብስ፥ ራስ ማሰሪያውንም፥ ዓይነ
ርግቡንም ያስወግዳል።
፳፬ እናም እንዲህ ይሆናል፣ በጥሩ ሽታ
ፈንታ ግማት፣ እና በመታጠቅያው ፈንታ
ᵐቀዳዳ፤ ጠጉርንም በመነቀስ ፈንታ መላ
ጣነት፤ ᵃበተብለጨለጨው ልብስ ፈንታ
ማቅ፤ በውበትም ፈንታ ᵃጠባሳ ይሆናል።
፳፭ ወንዶችሽ በሰይፍ ጀግኖችሽም
በውጊያ ይወድቃሉ።
፳፮ እናም በሮችዋ ያዝናሉ ያለቅሱ
ማል፤ እናም ተስፋ በመቁረጥ በመሬት
ላይ ብቻዋን ትቀመጣለች።

፳ ᵐ ኤር. ፱፡፲፩።
ᵃ ሰቆ. ፩፡፲።
፱ ᵐ ዘፍጥ. ፲፱፡፩፡ ፱–፲፡ ፳፩–፳፭።
ᵃ ቅ.መ.መ. ግብረ ሰዶማዊ ጸባይ።
፲ ᵐ ዘዳግ. ፲፪፡፳፰።
፲፪ ᵐ ኢሳ. ፱፡፲፯።
፲፫ ᵐ ዕብ. መከራከር። ሚክ. ፮፡፪፤ ት. እና ቃ. ፴፭፡፲–፭።
፲፬ ᵐ ዕብ. ገዢዎች ወይም መሪዎች።
ᵃ ኢሳ. ፭፡፯።
ᵃᵃ ᵐ ኔፊ ፳፰፡፲፤ ፲፪–፲፫።
ᵐ ይህም አጭበርብሮ ማግኘት ማለት ነው።
ᵐᵐ ዕብ. መጨረስ፣ ወይም መቃጠል።
፲፯ ᵐ ይህም በሽንገላ ጸባይ በአጭር፣ ፈጣን እርምጃ መሄድማለት ነው።
፲፯ ᵐ ዕብ. ማጋለጥ፤ “አሳፍራቸው” የሚል ትርጉም ያለው የአነጋገር ዘይቤ።
፲፰ ᵐ ምናልባት የጸጉር ማሰሪያ። ባለስልጣኖች በቁጥሮች ፲፰–፳፫ ውስጥ ስለተዘረዘሩት የሴት ጌጦች ምን እንደሆኑ አይስማሙም።
ᵃ ይህም እንደ ሩብ ጨረቃ ቅርጽ ያላቸው ጌጦች ማለት ነው።
፲፱ ᵐ ዕብ. መጋረጃዎች።
፳፪ ᵐ ዕብ. የሚያንጸባርቅ ልብስ።
፳፫ ᵐ ወይም ስስ ልብስ።
፳፬ ᵐ ዕብ. ቁራጭ ጨረቅ።
ᵃ ወይም ካባ።
ᵃᵃ ወይም መጥበስ (በባሪያ ቆዳ ላይ የሚደረግ ምልክት)።

ምዕራፍ ፲፬

ፅዮንና ሴቶች ልጆችዋ ይድናሉ፣ እናም በሺኛው ዘመን ይነፃሉ—ኢሳይያስ ፰ን አነጻፅሩ። ከ፩ኛ ፡ ፲፫–፲፭ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም በዚያ ቀን፣ ሰባት ሴቶች አን ድን ወንድ ይይዛሉ፣ የራሳችንን ዳቦ እን በላለን፣ እንዲሁም የራሳችንን ልብስ እን ለብሳለን፣ [ሀ]ሀፍረታችንን ለማስወገድ በስ ምህ ብቻ እንጠራ ይላሉ።

፪ በዚያ ቀን የጌታ [ለ]ቅርንጫፍ ያማረና የከ በረ ይሆናል፤ ከእስራኤል ለመጡት የምድ ሪቱ ፍሬ ታላቅና ውብ ይሆናል።

፫ እናም እንዲህ ይሆናል፣ በፅዮን የቀ ሩና በኢየሩሳሌም የቀሩ፣ በኢየሩሳሌም በሕያዋን መካከል የተመዘገቡ ሁሉ ቅዱስ ተብለው ይጠራሉ—

፬ ጌታ የፅዮንን ሴት ልጆች እድፍ [ሐ]ባጠበ [ሐ]ጊዜ፣ እና የኢየሩሳሌምንም ደም በፍርድ መንፈስና [ሐ]በሚያቃጥል መንፈስ ከመካከ ልዋ ባነፃ ጊዜ ቅዱስ ተብለው ይጠራሉ።

፭ እናም ጌታ በፅዮን ተራራ ባለ ማደ ሪያ ላይና፣ በመሰብሰቢያዎቿ ላይ፣ በቀን [ሀ]ደመናንና፣ ጢስን በሌሊትም የሚበራውን የእሳት ብርሃን ይፈጥራል፤ በፅዮን ክብር ሁሉ ላይ መጋረጃ ይሆናልና።

፮ እናም በቀን ከሙቀት ለመጠለያ ቦታ፣ [ሀ]ለመሸሸጊያም ቦታ፣ እናም ከውሽንፍርና ከዝናብ መሸፈኛ ድንኳን ይሆናል።

ምዕራፍ ፲፭

የጌታ የወይን አትክልት ስፍራ (እስራ ኤል) ባዶ ይሆናል፣ እናም የእርሱ ሕዝቦች ይበተናሉ—በአመፃና በመበተናቸው ጊዜ መከራ በእነርሱ ላይ ይመጣል—ጌታም ምልክቱን ያነሳል እናም እስራኤልን ይሰበ ስባል—ኢሳይያስ ፭ን አነጻፅሩ። ከ፭ኛ ፡ ፻፵፱–፭ኛ ፡ ፻፵፯ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም ከዚያ ለውድ ወዳጄ የወይን አት ክልት ስፍራውን በተመለከተ የወዳጄን [ሀ]ዘፈን እዘፍንለታለሁ። የእኔ ውድ ወዳጄ በጣም ፍሬያማ ኮረብታ ውስጥ የአትክልት ስፍራ አለው።

፪ እናም አጠረው፣ በውስጡ ያሉ ድን ጋዮችንም ሰብስቦ አወጣና፣ የተመረጠ ውን [ሀ]ወይን ተከለ፣ በመካከሉም ግንብን ገነባ፣ ደግሞም በውስጡ የወይን መጭመ ቂያ ሰራ፤ እናም ወይኑ ያፈራ ዘንድ ጠበ ቀው፣ የበረሃ ወይንንም አወጣ።

፫ እናም አሁን፣ በኢየሩሳሌም የምትኖ ሩና የይሁዳ ሰዎች ሆይ፣ በእኔና በወይን የአትክልት ስፍራዬ መካከል እንድትፈርዱ እጠይቃችኋለሁ።

፬ እኔ ያላደረግኩት በወይን የአትክልት ስፍራዬ ውስጥ ሊደረግ የሚገባ ነገር ምን ነበር? ስለዚህ፣ ወይን ያፈራል ብዬ በጠበ ቅሁት ጊዜ የበረሃ ወይንን አፈራ።

፭ እናም አሁን ሂዱ፤ የወይን አትክልት ስፍራዬን ምን እንደማደርገው እነግራች ኋለሁ—አጥሩን [ሀ]እነቅላለሁ፣ ይህም ይበ ላል፤ እናም በዚያ ያለውን ግድግዳ አፈር ሳለሁ፣ ለመራገጫም ይሆናል፤

፮ እናም እኔ አጠፋዋለሁ፤ አይከረከምም ወይም አይቆፈርም፤ ነገር ግን [ሀ]አረምና እሾህ ይበቅልበታል፤ እናም ደግሞ ደመ ናን በእርሱ ላይ [ለ]ዝናብ ደግመው እንዳያ ዘንቡ አዛለሁ።

፯ የሰራዊት ጌታ [ሀ]የወይን አትክልት ስፍራ

፲፬ ፩ *ሀ* ይህም ያላገባች እና ልጅ የሌላት የመሆን መጥፎ ስም ማለት ነው።
፪ *ሀ* ኢሳ. ፰፡፲፩፤ ፪ ኔፊ ፲፡፲፤ ያዕቆ. ፪፡፲፰።
፬ *ሀ* ቅ.መ.መ. ማጠብ፣ የታ ጠበ፣ የሚታጠቡ።
ለ ይህም ጌታ ምድርን በሚያ ጸዳበት ጊዜ ማለት ነው።
ሐ ሚል. ፫፡፪–፫፣ ፬፡፩።
፭ *ሀ* ዘፀአ. ፲፫፡፳፩።
፮ *ሀ* ኢሳ. ፳፭፡፬፣ ት. እና ቃ. ፻፲፭፡፮።
፲፭ ፩ *ሀ* ይህም የእግዚአብሔር ምህረትን እና የእስራኤል መልስ ለመስጠት ፍጥ ነት እንደሌላቸው በማሳየት ነቢይ የገጠመው የወይን አትክልት ስፍራ መዝሙር ወይም የምሳሌ ግጥም ማለት ነው።
፪ *ሀ* ኤር. ፪፡፳፩።
፫ *ሀ* መዝ. ፹፡፲፪።
፮ *ሀ* ኢሳ. ፯፡፳፫፣ ፴፪፡፲፫።
ለ ኤር. ፫፡፫።
፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. የጌታ የወይን አትክልት ስፍራ።

የእስራኤል ቤት ነውና፣ የደስታውም አት
ክልት የይሁዳ ሰዎች ናቸው፤ እናም ^ፍት
ህን ፈለገ፣ ነገር ግን እነሆ፣ ግፍ አየ፤ ፅድ
ቅን ፈለገ፣ ነገር ግን ልቅሶ ሰማ።

፳ ቦታ እስኪጠፋና እራሳቸው በም
ድር መካከል ″ብቻቸውን እስኪቀሩ ድረስ
^ቤትን ከቤት ለሚያገናኙ ወዮላቸው!

፳፩ የሰራዊት ጌታ እንዲህ ብሎ ሲምል በጆ
ሮዬ ሰማሁት፣ በእውነት ብዙ ቤቶች ባዶ
ይሆናሉ፣ እናም ታላቅና የሚያምሩ ከተሞ
ችም ያለነዋሪዎች ይሆናሉ።

፲ አዎን፣ ከወይኑ ቦታ አስር ጥማድ በሬ
ካረሰው አንድ ″የባዶስ መስፈሪያ ብቻ ይወ
ጣል፣ እናም አንድ የቆሮስ መስፈሪያ ዘር
አንድ የኢፍ መስፈሪያ ይሰጣል።

፲፩ በማለዳ ተነስተው ″ሃይለኛ መጠጥ
ለሚፈልጉ፣ እስከማታም ቀጥለው፣ እናም
^በወይን ለሚሰክሩ ወዮላቸው!

፲፪ እናም መሰንቆና፣ በገና፣ ከበሮና፣
እምቢልታም፣ የወይን ጠጅም በግብዣ
ቸው አለ፤ የጌታን ስራ ግን ″አልተመለከ
ቱም፣ እጁም ያደረገውን አላስተዋሉም።

፲፫ ስለዚህ፣ ሕዝቦቼ ምንም ″እውቀት
ስለሌላቸው በግዞት ተይዘዋል፤ እናም የተ
ከበሩት ሰዎቻቸው ተርበዋል፣ ሕዝቡም
ደግሞ በጥማት ደርቋል።

፲፬ ስለዚህ፣ ሲዖል ራሷን አስፍታለች፣
እናም አፍዋን ያለገደብ ከፍታለች፤ እናም
የእነርሱ ክብርና፣ ሕዝባቸው፣ ውበታቸ
ውም፣ እናም ያ የሚደሰተውም፣ ወደ እርሷ
ይወርዳል።

፲፭ እናም ተራው ሰው ዝቅ ይላል፣ ታላ
ቁም ሰው ትሁት ይሆናል፣ የኩራተኞች
ዐይን ትሁት ትሆናለች።

፲፮ ነገር ግን የሠራዊት ጌታ ″በፍርዱ ይከ
ብራል፣ እናም ቅዱስ የሆነው እግዚአብሔር
በፅድቁ ይቀደሳል።

፲፯ ከዚያም በጎቹ እንደተለመደው ይመ
ገባሉ፣ እንግዶችም የሰቡትን ባድማ ይበ
ላሉ።

፲፰ ″በግብዝነት ገመድ በደልን፣ እና
ኃጢያትንም በሰረገላ ማሰሪያ ^ይመስል
ወደ ራሳቸው ለሚሰቡ ወዮላቸው፤

፲፱ እናም ″ያፍጥን፣ ስራውን ያስቸ
ኩል፣ እኛ ^እንድናየው፤ እናም የእስራኤ
ሉን ቅዱስ ምክርም እኛ እናውቀው ዘንድ
ይቅረብ ለሚሉትም ወዮላቸው።

፳ መጥፎውን መልካም የሚሉ፣ እናም
ጥሩውን መጥፎ ″የሚሉ፣ ጨለማን ብር
ሃን፣ ብርሃንን ^ጨለማ፣ መራራውን
ጣፋጭ፣ ጣፋጩን መራራ ለሚሉትም
ወዮላቸው!

፳፩ በራሳቸው ዐይን ″ብልህና አስተዋይ
ለሆኑት ወዮላቸው!

፳፪ የወይን ጠጅ ለመጠጣት ኃያላንና፣
ጠንካራ መጠጦችን በመደባለቅ ለበረቱት
ሰዎች ወዮላቸው፤

፳፫ በደለኛውን ስለ ጉቦ ጻድቅ ለሚያደ
ርጉ፥ የጻድቁንም ″ጽድቅ ለሚያስወግዱ
በት ወዮላቸው!

፳፬ ስለዚህ፣ ″የእሳት ወላፈን ^ቃርሚ
ያን እንደሚበላ፣ እና ^እብቅም በነበል

፯ *ለ* ወይም ፍትህ።
፳ *ሀ* ይህም በብቻው እንዲኖር
መተው ማለት ነው።
ሀብታሙ የምድር ባልቤት
የደሀውን ትንሽ እርሻ
አጠቃሎ ይወስዳል።
ለ ሚክ. ፪፡ ፩–፪።
፲ *ሀ* ሕዝ. ፴፭፡ ፲–፲፩።
፲፩ *ሀ* ምሳ. ፳፫፡ ፴–፴፪።
ለ ቅ.መ.መ. የጥበብ ቃል።
፲፪ *ሀ* መዝ. ፳፰፡ ፭።
፲፫ *ሀ* ሆሴ. ፬፡ ፮።
ቅ.መ.መ. እውቀት።
፲፮ *ሀ* ቅ.መ.መ. ኢየሱስ
ክርስቶስ—ዳኛ።
፲፰ *ሀ* ቅ.መ.መ. ከንቱ፣ ከንቱነት።
ለ ይህም እንስሳት ለሸከማቸው
እንደሚታሰሩ እነርሱም
ከኃጢያቶቻቸው ጋር
ይተሳሰራሉ ማለት ነው።
፲፱ *ሀ* ኤር. ፲፯፡ ፲፩።
ለ ይህም እስከሚያዩት ድረስ
በመሲህ አያምኑም ማለት
ነው።
፳ *ሀ* ሞሮኒ ፯፡ ፲፡ ፲፰፤
ት. እና ቃ. ፳፡ ፲፯፤
፻፳፭፡ ፲፯።
ለ ፩ ዮሐ. ፩፡ ፯።
፳፩ *ሀ* ምሳ. ፫፡ ፭–፯፤
፪ ኔፊ ፳፰፡ ፲፫።
፳፫ *ሀ* ይህም የህግ መብቱን
ወሰዱበት ማለት ነው።
፳፬ *ሀ* አብድ. ፩፡ ፲፰፤
ሚል. ፬፡ ፩–፪፤
፪ ኔፊ ፳፡ ፲፯።
ለ ኢዩ. ፪፡ ፭፤
፩ ኔፊ ፳፪፡ ፲፭፣ ፳፫፤
፪ ኔፊ ፳፯፡ ፱፣ ፯፤
ት. እና ቃ. ፳፡ ፲፡ ፳፫–፳፬፤
፻፴፫፡ ፳፡ ፡
ሐ ሉቃ. ፫፡ ፲፯፤
ሞዛያ ፯፡ ፳፱–፴፩።

ባል እንደሚጠፉ፣ ስራቸው የበሰበሰ ይሆ
ናል፣ ቡቃያቸውም እንደትቢያ ይበናል፤
የእግዚአብሔርን የሰራዊት ጌታን ህግ ጥለ
ዋልና፣ የእስራኤሉንም ቅዱስ ቃል ″ንቀ
ዋልና።

፳፭ ስለዚህ፣ የጌታ ″ቁጣ በሕዝቡ ላይ
ነድዶአል፣ እጁንም በእነርሱ ላይ ዘርግ
ቷል፣ እናም መትቶአቸዋል፤ ተራሮች
ተንቀጥቅጠዋል፣ ሬሳዎቻቸውም በመ
ንገዶቻቸው መካከል ተከፍተዋል። በዚህ
ሁሉ ግን ቁጣው አልበረደችም፣ ነገር ግን
አሁንም እጁን እንደዘረጋ ነው።

፳፮ እናም ለሃገሮች ሁሉ ከሩቅ ″ምል
ክትን ያነሳል፣ ከምድር ዳርቻ ይመጡም
ዘንድ ^በፉጨት ይጠራቸዋል፤ እናም
እነሆ፣ እነርሱ እየተጣደፉ በፍጥነት ^ይመ
ጣሉ፤ በመካከላቸውም ደካማና ስንኩል
አይኖርም።

፳፯ የሚያንቀላፋም ሆነ የሚተኛ የለም፤
የወገባቸውም መቀነት አይፈታም፣ የጫ
ማቸውም ማሰሪያ አይበጠስም፤

፳፰ ፍላፃዎቻቸው ስለታም ይሆናሉ፣
ቀስቶቻቸውም ሁሉ ተወጥረዋል፣ የፈ
ረሶቻቸው ኮቴ እንደ ባልጩት እና ተሽ
ከርካሪዎቻቸውም እንደአውሎ ነፋስ ይቆ
ጠራሉ፣ ጩኸታቸውም እንደአንበሳ ነው።

፳፱ እንደ ″አንበሳ ደቦሎች ይጮሃሉ፤
አዎን፣ ይገሳሉም፣ ያዳኑአቸውንም አጥ
ብቀው ይይዛሉ፣ እና በጥንቃቄም ይዘዋ
ቸው ይሄዳሉ፣ ማንም አያድናቸውም።

፴ እናም በዚያ ቀን እንደ ባሕር ጩኸት
ይጮሁባቸዋል፤ ወደ ምድር ቢመለከቱ፣
እነሆ ጨለማና መከራን ይመለከታሉ፣
እናም ብርሃንም በዚያም ሰማያት ውስጥ
ጨልሟል።

ምዕራፍ ፲፮

*ኢሳይያስ ጌታን አየ—የኢሳይያስ ኃጢ
አቶች ይቅር ተብለዋል—እንዲተነ
ብይ ተጠርቷል—አይሁዶች የኢየሱስን
ትምህርት እንደሚያስወግዱ ተንብዮ
አል—ቅሪቶች ይመለሳሉ—ኢሳይያስ
ጌን አነጻፅሩ። ፳፻፶፬–፳፻፶፯ ም.ዓ. ገደማ።*

፩ ንጉስ ኡዝያን በሞተበት ″ዓመት፣ ጌታ
ደግሞ በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀ
ምጦ አየሁት፣ የልብሱም ^ዘርፍ መቅደሱን
ሞልቶት ነበር።

፪ ″ሱራፌልም ከእርሱ በላይ ቆመው
ነበር፤ እያንዳንዱ ስድስት ክንፍ ነበረው፤
በሁለቱ ክንፍ ፊቱን ሸፈነ፣ እናም በሁለቱ
ክንፍ እግሮቹን ሸፈነ፣ እናም በሁለቱ ክንፍ
ይበር ነበር።

፫ እናም አንዱ ለሌላኛው፥ ቅዱስ፣
ቅዱስ፣ ቅዱስ ነው የሰራዊት ጌታ፤ ምድር
ሁሉ በክብሩ ተሞልታለች፤ እያለ ይጮህ
ነበር።

፬ እናም ″የመዝጊያው ምሶሶ በጮኸው
ድምፅ ተናወጠ፣ እናም ቤቱ ጭስ ሞላበት።

፭ ከዚያም እኔ አልኩ፥ ወየው ለእኔ! ″የተ
በላሽሁ ነኝና፤ ምክንያቱም እኔ ከንፈረ-እር
ኩስ ነኝ፤ እናም ከንፈሮቻቸው በረከሰ ሕዝ
ቦች መካከል እኖራለሁ፤ ዐይኖቼም ንጉ
ሱን፣ የሰራዊት ጌታን አይተዋልና።

፮ ከሱራፌልም አንዱ ወደ እኔ እየበረረ
መጣ፣ በእጁም ከመሰዊያው በጉጠት የወ
ሰደው ″ፍም ነበር፤

፯ እናም በአፌ ላይ አደረገው፣ እናም
አለ፥ እነሆ፣ ይህ ከንፈሮችህን ነክቷል፣
″በደልህም ከአንተ ተወስዶአል፣ ኃጢያ
ትህም ተሰርዮልሀል።

፳፬ *መ* ፪ ሳሙ. ፲፪፡፯–፱።
፳፭ *ሀ* ት. እና ቃ. ፳፫፡፴፱፣ ፴፪፣ ሙሴ ፮፡፳፯።
፳፮ *ሀ* ቅ.መ.መ. ምልክት።
ለ ወይም ማፏጨት፣ ይህም ለመሰብሰብ የሚሰጥ ምልክት ማለት ነው። ኢሳ. ፯፡፲፰፣ ፪ ነፌ ፳፱፡፪።
ሐ ቅ.መ.መ. እስራኤል—የእስራኤል መሰብሰብ።
፳፱ *ሀ* ፫ ነፌ ፳፭፡፲፪–፲፫።
፲፮ ፩ *ሀ* ይህም በ፯፻፶ ም.ዓ. አካባቢ ማለት ነው።
ለ ይህም የልብሱ ጠርዝ ቅምቅማት፣ ወይም የዚህ ጫፍ ማለት ነው።
፪ *ሀ* ቅ.መ.መ. ኪሩቤል።
፬ *ሀ* ዕብ. የመግቢያ በር መሰረት ተንቀጠቀጠ።
፭ *ሀ* ዕብ. መቆረጥ፣ ይህም በእራሱ እና በህዝቡ ኃጢያት ህሊናው ተሸንፎ ነበር ማለት ነው።
፮ *ሀ* ይህም የማፅዳት ምሳሌ ማለት ነው።
፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. የኃጢያት ስርየት።

፳ ደግሞም የጌታን ድምፅ እንዲህ ሲል ሰማሁት፡ ማንን እልካለሁ፣ እናም ለእኛስ ማን ይሂድልን? እናም እኔ እንዲህ አልኩ፡ እነሆኝ፤ እኔን ላከኝ።

፳፩ እናም እርሱ አለኝ፡ ሂድና ይህንን ህዝብ ተናገራቸው—በእርግጥ ስሙ፣ ነገር ግን አይገባቸውም፤ እንዲሁም በእርግጥ እዩ፣ ነገር ግን አይገነዘቡም።

፲ የህዝቡን ልብ አደንድን፣ እናም ጆሮአቸውንም እንዳይሰማ፣ ዐይናቸውንም እንዳያዩ አድርግ—በዐይኖቻቸው እንዳያዩና በጆሮአቸውም ᵐእንዳይሰሙ፣ እናም በልባቸው እንዳያስተውሉና፣ ተመልሰውም እንዳይፈወሱ አድርግ።

፲፩ ከዚያም እኔ ጌታን እስከመቼ ድረስ ነው አልሁ? እናም እርሱ ከተሞች የሚኖሩባቸውን አጥተው እስኪፈርሱ፣ እና ቤቶችም ያለሰውና፣ ምድርም ፈፅሞ ባልጨት እስክትሆን ድረስ ነው አለኝ፤

፲፪ እግዚአብሔርም ሰዎችን ᵐእስኪያርቅ፡ በምድርም መካከል ውድማው መሬት ይበዛልና።

፲፫ ነገር ግን አንድ አስረኛው ይቀራል፣ እናም እነርሱ ይመለሳሉ፣ ቅጠሎቻቸውን ሲጥሉም ጉቶዎቻቸው በውስጣቸው እንደነበሩት ግራር እና እንደኮምበል ዛፍ ይበላሉም፣ ስለዚህ የተቀደሰው ዘር በዚያው ᵐጉቶው ይሆናል።

ምዕራፍ ፲፯

ኤፍሬምና ሶርያ በይሁዳ ላይ ጦርነ ትን አወጁ—ክርስቶስ ከድንግል ይወለ ዳል—ኢሳይያስ ፯ን አነጻፅሩ። ፳፻፶፱–፳፻፷፯ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ በአካዝ በኢዮአታም ልጅ ዘመን፣ በይሁዳ ንጉስ በኡዝያን ልጅ፣ የሶርያው ንጉስ ረአሶን፣ እና የሮሜልዩ ልጅ፣ የእስራኤልም ንጉስ ፋቁሔ ኢየሩሳሌምን ሊወጉ ወጡ፣ ነገር ግን ሊያሸንፉአትም አልቻሉም።

፪ እናም ለዳዊት ቤት ᵐከኤፍሬም ጋር ተባብራለች የሚል ወሬ ተነገረ። እናም የጫካ ዛፍ በንፋስ እንደሚናወጥ የእርሱ ልብና የህዝቡም ልብ ተናወጠ።

፫ ከዚያም ጌታ ኢሳይያስን አለው—አሁን አንተና ልጅህ ᵐያሱብ ከአካዝ ጋር ትገናኙት ዘንድ በልብስ አጣቢው እርሻ መንገድ ወዳለው ወደ ላይኛው የኩሬ መስኖ ጫፍ ውጡ፤

፬ እናም እንዲህ በለው—ተጠንቀቅ፣ ዝምም በል፣ ስለእነዚህ ስለሚጨሱ ስለሁለት ጥላሽቶች፣ ስለረአሶን በሶርያና፣ ሮሜልዩም ልጅ ቁጣ ᵐአትፍራ።

፭ ምክንያቱም ሶርያ፣ ኤፍሬምና የሮሜልዩም ልጅ በአንተ ላይ እንዲህ ሲሉ ክፉትን መክረዋልና፤

፮ ወደ ይሁዳ እንውጣና እናስጨንቀው፣ እናም ለራሳችን ᵐበእዚያም እንስበረው፣ በመካከሉም ንጉስ፣ አዎን፣ የጠብኤልንም ልጅ፣ እናስቀምጥ።

፯ እንዲሁም ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል—ይህ ምክር አይፀናም፣ አይሆንምም።

፰ የሶርያ ራስ ደማስቆ ነውና፣ እናም የደማስቆም ራስ ረአሶን ነውና፤ እናም በስድሳ አምስት ዓመት ውስጥ ኤፍሬም ይሰባበራል፣ ህዝብም አይሆንም።

፱ እናም የኤፍሬም ራስ ሰማርያ ነው፣ እናም የሰማርያ ራስ የሮሜልዩ ልጅ ነው። ᵐየማታምኑ ከሆነ በእርግጥ አትፀኑም።

፲ ከዚያም በላይ ጌታ አካዝን በድጋሚ እንዲህ ብሎ ተናገረው—

፲ ᵐ ማቴ. ፲፫፡፲፭–፲፭።
፲፪ ᵐ ፪ ነገሥ. ፲፯፡፲፰፣ ፳።
፲፫ ᵐ ይህም እንደ ዛፍ፣ ምንም እንኳን ቅጠሎቹ የተበተኑ ቢሆኑም፣ ህይወቱና ፍሬ የማፍራት ችሎታ በውስጥ አለው ማለት ነው።
፲፯ ᵐ ይህም ሰሜን እስራኤል በሙሉ በሰሜን ጎሳዎች መሪ በሆነው በኤፍሬም ስም ተጠርተዋል ማለት ነው።
፲፰ ᵐ ዕብ. የሚቀሩት ይመለሳሉ።
፱ ᵐ ይህም በጥቃቱ አትደንግጥ፤ እነዚያ ሁለት ንጉሶች የቀራቸው ትንሽ እሳት ነው ማለት ነው።
፲ ᵐ ዕብ. ተከፋፈሉት።
፱ ᵐ ፪ ዜና ፳፡፳።

፲፩ ከጥልቁ ወይም ከከፍታውም ቢሆን ከጌታ ከአምላክህ ᐸምልክትን ለምን።

፲፪ ነገር ግን አካዝም፣ አልለምንም፣ ጌታ ንም ᐸአልፈተንም አለ።

፲፫ እናም እርሱ አለ፡ የዳዊት ቤት ሆይ፣ አሁን ስሙኝ፤ በእውነት ሰውን ማድከም ቀላል ሆነባችሁ፣ ግን አምላኬን ደግሞ ልታደክሙ ነውን?

፲፬ ስለዚህ፣ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣ ችኋል—እነሆ፣ ᐸድንግል ትፀንሳለች፣ እናም ወንድ ልጅም ትወልዳለች፣ ስሙ ንም ᐸአማኑኤል ብላ ትጠራዋለች።

፲፭ እርሱም ክፉን ለመጥላትና መልካ ሙን ለመምረጥ ማወቅ ይችል ዘንድ ቅቤና ማር ይበላል።

፲፮ ᐸህፃን መጥፎውን ከመጥላቱና ጥሩውን ከመምረጡ በፊት፣ የጠላኸው መሬት በሁ ሉም ᐸነገሥታቶች ይተዋል።

፲፯ ጌታ ᐸኤፍሬም ከይሁዳ ከተለየበት ቀን ጀምሮ ያልመጣውን ዘመን በአንተና በሕ ዝብህ በአባትህም ቤት ላይ ᐸያመጣል፤ እር ሱም የአሦር ንጉሥ መምጣት ነው።

፲፰ እናም በዚያ ቀን እንዲህ ይሆናል ጌታ በግብፅ ዳርቻ ያለውን ዝንብ እና በአሶር ምድር ያለውን ንብ ᐸበፉጨት ይጠራል።

፲፱ እናም ይመጣሉ፣ እነርሱም ሁሉ በበረሃ ሸለቆ፣ እና በድንጋይም ዋሻና በእ ሾህ ላይ ሁሉ፣ በቁጥቋጦውም ሁሉ ላይ ያርፋሉ።

፳ በዚያም ቀን ጌታ ከወንዙ ባሻገር፣ በቀ ጠራቸው ᐸበአሶር ንጉስ፣ የራስና የእግሩን ጠጉር ᐸይላጫል፣ እናም ምላጩ ደግሞ ጢሙን ይበላል።

፳፩ እናም በዚያ ቀን እንዲህ ይሆናል፣ አንድ ሰው ጊደርና ሁለት በጎችን ᐸይመ ግባል፤

፳፪ እናም እንዲህ ይሆናል፣ ከሚሰጡት ወተት ብዛት የተነሳ እርሱ ቅቤን ይበላል፣ በሀገሪቱም መካከል የቀረ ማንም ሰው ቅቤና ማር ይበላል።

፳፫ እናም በዚያ ቀን እንዲህ ይሆናል፣ ሺህ ᐸብር የሚያወጣው ሺህ የወይን ግንድ በነበረበት ቦታ ሁሉ ኩርንችትና እሾህ ብቻ ይሆናሉ።

፳፬ በምድሪቱ ሁሉ ኩርንችትና እሾህ በመሆኑ ሰዎች በፍላፃና በቀስት ወደዚያ ይመጣሉ።

፳፭ እናም በመቆፈሪያ ወደ ተቆፈሩ ኮረብ ቶች ሁሉ፣ ከኩርንችትና እሾህ ፍርሀት ወደ ዚያ ማንም አይሄድም፤ ነገር ግን የበሬ ማሰ ማሪያና ᐸየታናሽ ከብት መረገጫ ይሆናል።

ምዕራፍ ፲፰

ክርስቶስ እንደማሰናከያ ዓለት እና እንቅ ፋት ይሆናል—ጠንቋይን ሳይሆን ጌታን እሹ—ለመመሪያችሁ በህጉና በምስክር ነቱ ላይ ተስፋ አድርጉ—ኢሳይያስ ፲ን አነጻፅሩ። ከ፲፣፲፯፱–፲፣፲፰፲ ም.ዓ. ገደማ።

፩ ከዚህም በላይ፣ የጌታ ቃል እንዲህ አለኝ—ትልቁን ጥቅል ውሰድ፣ እናም ᐸማሔር-ሻላል-ሽሽ-ባዝ ብለህ በሰው ብዕር ፃፍበት።

፪ እናም እኔ የታመኑ ᐸምስክሮችን፣ ካህን ኦርዮን እና የበራክዩን ልጅ ዘካርያ ስን ለምዝገባው ወደ እኔ ወሰድሁ።

፲፩ ᐸ ቅ.መ.መ. ምልክት።
፲፪ ᐸ ይህም ፈትን፣ ሞክር፣ ወይም እርግጠኛ አድርግ ማለት ነው።
፲፬ ᐸ ቅ.መ.መ. ድንግል።
ለ ዕብ. ከእኛ ጋር እግዚአብሔር ነው።
ቅ.መ.መ. አማኑኤል።
፲፮ ᐸ ፪ ኔፊ ፲፰፡፴።
ለ ፪ ነገሥ. ፲፭፡፴፣ ፲፮፡፴።
፲፯ ᐸ ፩ ነገሥ. ፲፪፡፲፮–፲፱።
ለ ፪ ዜና ፳፰፡፲፱–፳፩።
፲፰ ᐸ ወይም ማፏጨት፣ ይህም ምልክት መስጠት፣ መጥራት ማለት ነው።
ኢሳ. ፭፡፳፮።
፳ ᐸ ፪ ነገሥ. ፲፮፡፭–፱።
ለ ይህም ምድሯ ከውጪ በሚመጡ ወራሪዎች ህዝቧ በሙሉ ይጠፋሉ ማለት ነው።
፳፩ ᐸ ይህም ለሚተርፉት እራሳቸውን ለመደገፍ የሚችሉ ብቻ ይቀራሉ ማለት ነው።
፳፫ ᐸ ወይም የብር ቁራጭ።
፳፭ ᐸ ዕብ. በጎች ወይም ፈየሎች።
፲፰ ᐸ ዕብ. ወደ ብዝበዛው በፍጥነት ለመድረስ፣ የሚታደነውን አጣደፈ።
፪ ᐸ ቅ.መ.መ. ምስክር።

፲ እናም እኔ ወደ ᵐነቢይቱ ቀረብሁ፤ እር ሷም ፀነሰች እናም ወንድ ልጅ ወለደች። ከዚያም ጌታ እንዲህ አለኝ፥ ማኻር-ሻላል-ሐሽ-ባዝ ብለህ ስሙን ጥራው።

፱ እነሆም፣ ᵐህፃኑ አባቱንና እናቱን መጥራት ᵃሳያውቅ፣ የደማስቆን ሀብትና የሰማርያን ᵃሙርኮ በአሶር ንጉስ ፊት ይወስዳል።

፰ ጌታ እንደገና ደግሞ እንዲህ ሲል ተናገረኝ፥

፯ ይህ ህዝብ በቀስታ የሚሄደውን ᵐየሰሊሆምን ውሃ እስከጠሉ፣ እናም ᵃበረአሶንንና በሮሜልዩም ልጅ በመደሰታቸው የተነሳ፤

፯ ስለዚህ አሁን፣ እነሆ፣ ጌታ ብርቱና ብዙ የሆነውን የወንዝ ውሃ፣ የአሶርን ንጉስና ክብሩን ሁሉ ᵐያመጣባቸዋል፤ እናም እርሱ መስኖዎችን ሁሉ ይሞላል፣ እናም በዳርቻውም ሁሉ ላይ ይፈስሳል።

፰ እናም በይሁዳ ᵐያልፋል፤ እያጥለቀለቀም ያልፋል፣ እስከ አንገትም ይደርሳል፤ እናም ᵃአማኑኤል ሆይ፣ የክንፉ መዘርጋት የአገርህን ስፋት ትሞላለች።

፱ ህዝብ ሆይ ᵐተባበሩ፣ እናም በትንንሹ ትከፋፈላላችሁ፤ እናንተም ሩቅ ሀገር ያላችሁ ሁሉ አድምጡ፤ ራሳችሁን አስታጥቁ፣ እናም በትንንሹ ትከፋፈላላችሁ፤ ራሳችሁን አስታጥቁ፣ እናም በትንንሹ ትከፋፈላላችሁ።

፲ በአንድነት ተመካከሩ፣ እናም እርሱ ከንቱ ይሆናል፤ ቃሉን ተናገሩ፣ እናም አት ፀናም፣ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ᵐነውና።

፲፩ ጌታ በፅኑ እጁ እንዲሁ ተናግሮኛልና፣ እናም በዚህ ህዝብ መንገድ እንዳልራመድ እንዲህ ሲል አዘዘኝ፥

፲፪ ይህ ህዝብ ግብረ-አበራዊ ነው በሚለው ሁሉ ᵐግብረ-አበራዊ ነው አትበሉ፣ መፈራታቸውንም ቢሆን አትፍሩ፣ አትደንግጡ።

፲፫ የሰራዊት ጌታ እራሱን ቀድሱት፣ እናም የእናንተ ፍርሃት ᵐእርሱ ይሁን፣ ስጋታችሁም እርሱ ይሁን።

፲፬ እናም እርሱ ᵐመሸሸጊያ፤ ነገር ግን ለሁለቱ ለእስራኤል ቤቶች፣ ለእንቅፋት ድንጋይና፣ ለማሰናከያ ᵃአለት፣ በኢየሩሳሌምም ለሚኖሩ ለወጥመድና ለአሽክላ ይሆናል።

፲፭ እናም ብዙዎች ከእነርሱ ጋር ᵐይሰናከላሉ እንዲሁም ይወድቃሉ፣ ይሰበራሉም፣ ይጠመዳሉም፣ እናም ይማረካሉ።

፲፮ በደቀ መዛሙርቶቼም መካከል ምስክርነትን እሰር፣ ᵐህጉንም አትም።

፲፯ እናም ከያዕቆብ ቤት ፊቱን ᵐየደበቀውን ጌታ እጠብቃለሁ፣ እናም እርሱን እፈልገዋለሁ።

፲፰ እነሆ፣ እኔና ጌታ የሰጠኝ ልጆቼ በእስራኤል በፅዮን ተራራ ከሚኖረው ከሰራዊት ጌታ ዘንድ ᵐምልክትና ተአምራት ነን።

፲፱ እናም የሚጮሁትንና፣ ድምፃቸውን ዝቅ አድርገው ᵐየሚናገሩትን መናፍስት ጠሪዎችንና ᵃጠንቋዮችን ጠይቁ ባሉአችሁ ጊዜ—ለህያዋን ᶜከሙታን ለመስማት ህዝቡ ከአምላኩ መጠየቅ ᶜአይገባውምን?

፳ ወደህግና ወደምስክርነት ተመልከቱ፣

፲ ᴴ ይህም ባለቤቱ ማለት ነው።
፱ ᴴ ፪ ኔፊ ፲፯፡፲፯።
ᵃ ኢሳ. ፰፡፱።
ᶜ ፪ ነገሥ. ፲፭፡፳፱።
፯ ᴴ ዘፍጥ. ፵፱፡፲፣ ጆ.ስ.ት. ዘፍጥ. ፶፡፳፱ (ተጨማሪ)።
ᵃ ኢሳ. ፯፡፩።
፯ ᴴ ይህም በመጀመሪያ በሰሜን አስራኤል ላይ ማለት ነው።
፰ ᴴ ይህም አሶር ወደ ይሁዳ ዘልቆ ይገባል ማለት ነው።
ᵃ ቅ.መ.መ. አማኑኤል።
፱ ᴴ ይህም ህብረትን መፍጠር ማለት ነው።
፲ ᴴ ይህም ይሁዳ (የአማኑኤል ምድር) ይተርፋል ማለት ነው።
መዝ. ፵፮፡፯።
፲፪ ᴴ ይህም ይሁዳ ለደህንነት ከሌሎች ጋር በሚሰራው የሚስጥር ሴራ ላይ መመካት አይገባውም ማለት ነው።
፲፫ ᴴ ይህም በእግዚአብሔር ፊት አምልኮን የሚያሳይ እና ትሁት ሁን ማለት ነው።
፲፬ ᴴ ሕዝ. ፲፩፡፲፮–፳፩።
ᵃ ፩ ጴጥ. ፪፡፭–፰፣ ያዕቆ. ፬፡፲፩–፲፮።
፲፭ ᴴ ማቴ. ፳፩፡፴፪–፴፬።
፲፮ ᴴ ዕብ. ትምህርት። ቅ.መ.መ. ወንጌል።
፲፯ ᴴ ኢሳ. ፶፬፡፰።
፲፰ ᴴ ይህም የኢሳይያስ እና የወንድ ልጆቹ ስም በመከታተል፥ “ያህዌ ያድናል”፣ “የሚቀረው ይመለሳል”፣ እና “ወደ ብዝበዛው በፍጥነት ለመድረስ፣ የሚታደነውን አጣደፈ” ማለት ነው።
፪ ኔፊ ፲፯፡፲፣ ፲፰፡፲፣ ፲፱፡፲።
፲፱ ᴴ ዘሌዋ. ፳፡፮።
ᵃ ይህም ጠንቋዮች፣ ምዋርተኞች ማለት ነው።
ᶜ ወይም ለ. . .ጥቅም ማለት ነው።
መ ፩ ሳሙ. ፳፰፡፮–፳።

እናም በዚህ ቃል መሰረት ᵐካልተናገሩ፣ ምክንያቱ ብርሃን በውስጣቸው የለም።

፳፩ እነርሱም ይህን በጣም ተጨንቀውና ተርበው ᵐያልፋሉ፤ እናም እንዲህ ይሆናል በተራቡ ጊዜ፣ በጣም ይቆጣሉ፣ እናም አምላካቸውንና ንጉሳቸውን ይረግማሉ፣ ወደ ላይም ይመለከታሉ።

፳፪ እናም ወደ ምድር ይመለከታሉ፣ እናም ችግርን፣ ጨለማን፣ የሚያስጨንቅ ጭጋግን ያያሉ፣ እናም ወደ ጨለማም ይሰ ደዳሉ።

ምዕራፍ ፲፱

ኢሳይያስ ስለመሲሁ ተናገረ—በጨለማ ያለ ሕዝብ ታላቅ ብርሃን ያያል—ህፃን ልጅ ተወልዶልናል—እርሱም የሠላም አለቃ ይሆናል በዳዊትም ዙፋን ላይ ይነ ግሳል—ኢሳይያስ ፱ን አነጻፅሩ። ከ፳፪፻፶፱–፳፪፻፶፯ ም.ዓ. ገደማ።

፩ ይሁን እንጂ፣ ጭጋግም በጭንቀት በነበረሽ አይነት አይሆንም፣ በመጀመሪያ ᵐየዛብሎንንና የንፍታሌምን ምድር በቀላል መታ፣ እና በኋላ ግን በዮርዳኖስ በስተጀርባ ያሉትን የገሊላ ሀገሮች በቀይ ባህር አም ርሮ መታ።

፪ ᵐበጨለማ የሄደ ህዝብ ታላቅ ብርሃን አየ፤ በሞት ጥላ ምድርም ለኖሩት ብርሃን ወጣላቸው።

፫ ህዝብህን አብዝተሃል፣ ደስታንም ᵐጨምረሃል—በመከር ደስ እንደሚላቸው፣ እና ምርኮንም ሲካፈሉ ደስ እንደሚላቸው ሰዎች በፊትህ ደስ ይላቸዋል።

፬ አንተም የሸክሙን ቀንበር፣ የጫንቃው ንም በትር፣ የአስጨናቂውንም በትር ሰብ ረሃልና።

፭ ሁሉም የተዋጊው ጦርነት በሁከት የተ ሞላ ነውና፣ እናም ልብሶች በደም ተጨ ማልቀዋል፤ ነገር ግን ይህኛው በመቃጠ ልና በእሳት ማቃጠያ ይሆናል።

፮ ᵐህፃንም ተወልዶልናልና፣ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ ᶮአለቅነትም በጫን ቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ፣ መካሪ፣ ᵒሀያል አምላክ፣ ᵐየዘለአለም አባት፣ ᵐየሠላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።

፯ ከዛሬ ጀምሮ እስከዘለዓለም ድረስ በፍ ርድና በፅድቅ ያፀናውና ይደግፈው ዘንድ፣ በዳዊት ዙፋንና ᵐበመንግሥቱ ላይ አለቅነቱ ይበዛል፣ ለሰላሙም ፍፃሜ ᶮአይኖረውም። የሰራዊት ጌታ ቅንዐት ይህንን ያደርጋል።

፰ ጌታ ቃሉን ለያዕቆብ ላከ ᵐበእስራኤ ልም ላይ ወደቀ።

፱ እናም ሁሉም ህዝብ ኤፍሬምም ቢሆን እንኳ እናም የሰማርያ ሰዎች፣ በትዕቢትና በኩራት እንዲህ የሚሉት ሁሉ ያውቃሉ፤

፲ ጡብ ወድቋል፣ ነገር ግን በተወቀረ ድንጋይ እንሰራለን፣ የሾላው ዛፍ ተቆ ርጦአል፣ ነገር ግን በዝግባ እንተካዋለን።

፲፩ ስለዚህ ጌታ ᵐበረአሶን ላይ ጠላቶችን ያስነሳል፣ ጠላቶቹንም በአንድነት ይሰበ ስባል።

፲፪ ሶርያን ከፊትና ፍልስጤምን ከኋላ፤ እናም እስራኤልን በተከፈተ አፍ ᵐይበሉአ ታል። በዚህ ሁሉ እንኳን ᶮቁጣው አልበ ረደችም፣ ነገር ግን አሁንም እጁን እንደ ዘረጋ ነው።

፲፫ ወደ እርሱ ᵐያልተመለሱት ተመተ ዋልና፣ የሰራዊት ጌታንም አልፈለጉም።

፳ ᵐ ይህም ከሙታን ጋር የሚነጋገሩበት (ደግሞም በቁጥር ፳፩–፳፪) ማለት ነው።

፳፩ ᵐ ይህም እስራኤል ስለማያዳምጡ እንደ ምርኮ ይወሰዳሉ ማለት ነው።

፲፱ ፩ ᵐ ማቴ. ፬፡፲፫–፲፮።

፪ ᵐ "ደብዛዛነት" እና "ጭለማነት" ክህደት እና ምርኮነት ናቸው፤ "ታላቁ ብርሀን" ክርስቶስ ነው።

፫ ᵐ ኢሳ. ፱፡፲፱። ᶮ ᵐ ኢሳ. ፯፡፲፱፤ ሉቃ. ፪፡፲፩።

ᵒ ማቴ. ፳፫፡፲፤ ᵐ ማቴ. ፳፡፲–፲፩።

ᶮ ᵐ ቅ.መ.መ. መንግስት።

ᵒ ዳን. ፪፡፴፭።

ᵐ ᵐ ይህም ከዚህ የሚቀጥለው የነቢይ መልእክት (ቁጥሮች ፳–፳፩) እስራኤል ተብሎ ለሚጠሩት ለእስሩ ጎሳዎች የተሰጠ መልእክት ነበር ማለት ነው።

፲፩ ᵐ ᶮ ነገሥ. ፲፯፡፭–፱።

ᵒ ᶮ ነገሥ. ፲፯፡፯፤ ፲፡፱።

ᵐ ᵐ ኢሳ. ፭፡፳፭፤ ፲፡፱።

፲፫ ᵐ ዓሞ. ፱፡፯–፲፪።

፲፡ ስለዚህ ጌታ ራስንና ጅራትን፣ ቅርን ጫፍና እንግጫን ከእስራኤል በአንድ ቀን ይቆርጣል።

፲፩ ሽማግሌው እርሱ ራስ ነው፣ ሀሰትን የሚያስተምረው ነቢይ እርሱ ጅራት ነው።

፲፪ የዚህ ህዝብ መሪዎች ህዝቡን እንዲ ሳሳት ያደርጉታልና፣ እናም ተመሪዎቹ ደግሞ ይጠፋሉ።

፲፫ ሰው ሁሉ ግብዝና ክፉ ሰሪ ነውና፣ አፉም ሁሉ *ᵐስንፍናን ይናገራልና፣ ስለ ዚህ ጌታ በወጣቶቻቸው ደስ አላለውም፣ አባት ለሌላቸውና ለመበለቶችም *ᵃምህረት አይኖረውም። በዚህም ሁሉ እንኳን ቁጣው አልበረደለትም፣ ነገር ግን *ᵃእጁ ገና ተዘር ግታለች።

፲፬ ኃጢያት እንደእሳት ትቃጠላለችና፤ ይህም ኩርንችቱንና እሾህንም ትበላለች፣ እና ጥቅጥቅ ያለውንም ጫካ ታቃጥላለች፣ እናም እንደጢስም ወደ ላይ ይነሳሉ።

፲፭ በሰራዊት ጌታ ቁጣ የተነሳ ምድር ትጨልማለች፣ ሰዎች ለእሳቱ እንደማገዶ ይሆናሉ፣ *ᵐማንም ሰው ወንድሙን አያድ ንም።

፲፮ እና እርሱ በቀኙ እጅ ይመነጭቃልና ይራብማል፤ በግራ እጅም *ᵐይበላል አይ ጠግቡምም፤ እያንዳንዱም የራሱን ክንድ ስጋ ይበላል—

፲፯ *ᵐምናሴ፣ *ᵃኤፍሬም፤ እናም ኤፍ ሬም፣ ምናሴ፤ እነርሱ በአንድነት *ᵃበይ ሁዳ ላይ ይነሳሉ። ይህም ሁሉ ተፈፅሞ እን ኳን ቁጣው ገና አልበረደችምና፣ ነገር ግን አሁንም እጁ ተዘርግታለች።

ምዕራፍ ፳

የአሶር መጥፋት ኃጢአተኞች በዳግም ምፅአት እንደሚጠፉት ምሳሌ ነው—ጌታ እንደገና ከመጣ በኋላ ጥቂት ሰዎች ይቀ ራሉ—የያዕቆብ ቅሪቶች በዚያን ቀን ይመ ለሳሉ—ኢሳይያስ ፲ን አነጻፅሩ። ከ፳፻፶–፳፻፸ ም.ዓ. ገደማ።

፩ ጻድቅ ያልሆኑ ሕጎችን ለሚደነግጉ፣ የጻፉአቸውን የግፍን ትእዛዛት ለሚያዝዙ ወዮላቸው፤

፪ *ᵐፍትህ የሚፈልጉትን ለመከልከል፣ እናም የድሃ ሕዝቦቼን መብት ለመውሰድ፣ *ᵃመበለቶችንም ሰለባቸው እንዲሆኑላቸው፣ እናም አባት አልባዎችን ለመዝረፍ ዘንድ የግፍን ትእዛዛት አዝዘዋል!

፫ እናም ከሩቅ በሚመጡት *ᵐበመጎብኘ ታችሁና በመውደሚያችሁ ቀን ምን ታደ ርጋላችሁ? ለእርዳታስ ወደ ማን ትሸሻላ ችሁ? ክብራችሁንስ ወዴት ትተዋታላችሁ?

፬ ከእኔ ውጭ ከእስረኞች በታች ይጎነበ ሳሉ፣ በሚገደሉትም መካከል ይወድቃሉ። በዚህም ሁሉ እንኳን ጌታ ቁጣው አልበረ ደችም፣ ነገር ግን አሁንም ገና እጁ ተዘር ግታለች።

፭ ሶርያ ሆይ፣ የቁጣዬ በትር፣ እናም በእ ጃቸው ያለው መሳሪያ *ᵐቁጣቸው ነው።

፮ *ᵐበግብዝ ሀገሮችም መካከል እልከዋ ለሁ፣ እናም ምርኮንና ብዝበዛውንም ይወ ስድ ዘንድ፣ እና እንደ አደባባይ ጭቃ የተ ረገጡ ይሆኑ ዘንድ በተቆጣሁአቸው ህዝብ ላይ እልከዋለሁ።

፯ ነገር ግን እርሱ ይህን አላቀደውም፣ ልቡም ቢሆን እንደዚህ አያስብም፤ በልቡ ውስጥ ያለው ግን ብዙ ሀገሮችን ለማጥፋ ትና ለመቁረጥ ነው።

፰ እንዲህ ይላል፥ መሳፍንቶቼ ሁሉ ነገ ሥታት አይደሉምን?

፱ ካልኖ እንደ ከርከሚሽ አይደለችምን? ሐማትስ እንደ አርፋድ አይደለችምን? ሰማርያስ እንደ ደማስቆ አይደለችምን?

፲ የተቀረፁ ምስሎቻቸው ከኢየሩሳሌምና

፲፯ *ሀ* ፪ ኔፊ ፱፡፳፰–፳፱።
ለ ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።
ሐ ያዕቆ. ፭፡፣ ፣ ፤ ፡ ።
፲፱ *ሀ* ሚክ. ፯፡ ፡–፯።
፳ *ሀ* ዘዳግ. ፳፰፡ ፣ ፣–ፍ፣ ።
፳፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. ምናሴ።
ለ ቅ.መ.መ. ኤፍሬም።
ሐ ቅ.መ.መ. ይሁዳ፣ የያዕቆብ ልጅ።
፳፪ *ሀ* ወይም ፍትህ።
ለ ቅ.መ.መ. ባል የሞተባት።
፫ *ሀ* ይህም ቅጣት ማለት ነው።
፭ *ሀ* ኢሳ. ፣ ፡ ።
፮ *ሀ* ይህም እስራኤልን የሚ.ቃወም ማለት ነው።

ከሰማርያ ምስሎች የበለጡትን፣ የጣዖቶችን መንግስታት [a]እጄ እንዳገኘች፤

፲፩ በሰማርያና በጣዖቶቿ እንደአደረግሁት በኢየሩሳሌምና በጣዖቶቿ አላደርግምን?

፲፪ ስለዚህ እንዲህ ይሆናል ጌታ ስራውን በሙሉ በፅዮን ተራራና በኢየሩሳሌም ሲፈፅም፣ [a]የአሶርን ንጉስ የኩሩ ልብ [b]ፍሬውን የዐይኑንም ከፍታ ትምክህት እቀጣለሁ።

፲፫ [a]እርሱ እንዲህ ብሎአልና፤ በእጄ ጥንካሬና በጥበቤ እነዚህን ነገሮች አድርጌአለሁ፤ እኔ አስተዋይ ነኝና፤ የህዝቦችንም ድንበር ገፋሁ፣ ሀብታቸውንም ዘረፍኩ፣ እናም እንደ ጀግና ሆኜ ፍጥረታትን አጠቃሁ፤

፲፬ እናም እጄ የህዝብን ሀብት እንደ ወፍ ጎጆ አገኘች፤ እና በሰው የተተዉትን እንቁላሎች እንደሚሰበስብ እኔም ደግሞ ምድርን በሞላ ሰበሰብኩ፤ ክንፉን የሚያራግብ፣ ወይም አፉን የሚከፍትም ሆነ የሚጮህ ማንም የለም።

፲፭ [a]ምሳር የሚጠቀምበትን ሰው እበልጣለሁ ብሎ [b]ይመካልን? ወይስ መጋዝ በሚስበው ላይ እራሱን ያጎላልን? በትርስ በራሱ ያለእጅ እራሷን እንደምትነቀንቅ ወይንም ከዘራ እንጨት እንዳልሆነ ሁሉ እራሱን እንደሚያነሳ!

፲፮ ስለዚህ ጌታ፣ የሰራዊት ጌታ፣ በወፍራሞቹ ላይ መክሳትን ይልካል፣ [a]ከክብሩም በታች እንደ እሳት መቃጠል የሆነ ቃጠሎን ያስነሳል።

፲፯ እናም የእስራኤል ብርሃን ለእሳት ይሆናል፣ ቅዱሷም ነበልባል ይሆናል፣ እሾሁንና ኩርንችቱንም በአንድ ቀን ያቃጥለዋል፣ ይበላዋልም፤

፲፰ እናም የዱሩንም፣ የፍሬያማውን ሜዳ፣ ክብሩንም፣ ነፍሱንና ስጋውንም [a]ያቃጥለዋል፤ እነርሱ አርማ ተሸካሚው እንደ ወደቀ ይሆናሉ።

፲፱ እናም [a]የተቀሩትም የዱር ዛፎቹ ህፃን መቁጠር እስኪችላቸው ድረስ ትንሽ ይሆናሉ።

፳ እናም [a]በዚያ ቀን እንዲህ ይሆናል፣ የእስራኤል ቅሪት፣ እናም [b]ከያዕቆብ ቤት የዳኑት፣ ከእንግዲህ ወዲህ በዚያ በመታቸው ላይ [c]አይቆዩም፣ ነገር ግን በጌታ በእስራኤሉ ቅዱስ በእውነት ይመካሉ።

፳፩ [a]ቅሪቶች ይመለሳሉ፣ አዎን፣ የያዕቆብም ቅሪቶች ቢሆኑ እንኳ፣ ወደ ኃያሉ እግዚአብሔር ይመለሳሉ።

፳፪ እስራኤል ሆይ ህዝብሽ እንደ ባህር አሸዋ የበዛ ቢሆንም እንኳ፣ ቅሪቶቻቸው ይመለሳሉ፤ የተነገረውም [a]ጥፋት በፅድቅ [b]ይትረፈረፍል።

፳፫ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር ያለቀ [a]የተቈረጠ ነገርን በምድር ሁሉ መካከል ይፈጽማል።

፳፬ ስለዚህ፣ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል—በፅዮን የምትኖሩ ህዝቤ ሆይ፣ አሶርን አትፍራው፤ በበትር ይመታሀል፣ ግብፅም [a]እንዳደረገው ዘንጉን ያነሳብሀል።

፳፭ ቁጣዬ እስኪፈፀም መዓቴም እስኪ ያጠፋቸው ጥቂት ጊዜ ቀርቷል።

፲ *a* ይህም የአሶር ንጉስ እጅ (ቁጥሮች ፲–፲፩) ማለት ነው።

፲፪ *a* ሶፎ. ፪ ፡ ፲፫።
b ይህም በኩራት ማጉራት ማለት ነው።

፲፫ *a* ይህም የአሶር ንጉስ (ቁጥሮች ፲፫–፲፭) ማለት ነው።

፲፭ *a* ይህም ንጉሱ እግዚአብሔርን በመቃወም ይበለጽጋልን? ማለት ነው።
b በዚህ ቁጥር ውስጥ ያሉ ምሳሌዎች አንድ አይነት ጥያቄ ይጠይቃሉ፥ ሰም (ለምሳሌ የአሶር ንጉስ) እግዚአብሔርን በመቃወም ሊበለፅግ ይችላል?

፲፮ *a* ይህም የአሶር ንጉስ (ደግሞም ቁጥሮች ፲፯–፲፱) ማለት ነው።

፲፰ *a* ይህም አሶር በሙሉ ትጠፋለች ማለት ነው።

፲፱ *a* ይህም የቀሩት የአሶር ጦር ሰራዊት ማለት ነው።

፳ *a* ይህም በኋለኛው ቀናት ማለት ነው።
b ዓሞ. ፱ ፡ ፳–፳።
c ይህም መመካት ማለት ነው።

፳፩ *a* ኢሳ. ፲፩ ፡ ፲፩–፲፪።

፳፪ *a* ት. እና ቃ. ፳፫ ፡ ፴፩። ቅ.መ.መ. አለም—የአለም መጨረሻ።
b ይህም ቅጣቱ ሲመጣ፣ ምህረት ይገኛል ማለት ነው።

፳፫ *a* ይህም የታወጀውን ጥፋት አመጣ ማለት ነው።

፳፬ *a* ይህም ግብጻውያን ወደፊት እንደሚያደርጉት ማለት ነው። ዘፀአ. ፭ ፡ ፲፫–፲፱።

፲፪ ሀ ቅ.መ.መ. የሰለስቲያል
ክብር።
፲፫ ሀ ኢሳ. ፳፱፡፱፣
፪ ኔፊ ፳፯፡፲፯።
፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. መፅሐፍ ቅዱስ።
ለ ቅ.መ.መ. መፅሐፈ ሞርሞን።
ሐ ፪ ኔፊ ፳፱፡፲፩፣
ኤተር ፱፡፳–፣።
፲፭ ሀ ቃላት ፩፡፲፩።

መፅሐፈ ያዕቆብ

የኔፊ ወንድም

ለወንድሞቹ የሰበካቸው ቃላት። እርሱ የክርስቶስን ትምህርት ለማጥፋት የተመኘውን ሰው አሳፈረው። የኔፊን ህዝብ ታሪክ በተመለከተ ጥቂት ቃላት።

ምዕራፍ ፩

ያዕቆብና ዮሴፍ ሰዎች በክርስቶስ እንዲ ያምኑና ትዕዛዛቱን እንዲጠብቁ ለማሳመን ሞከሩ—ኔፊ ሞተ—ክፋት በኔፋውያን መካከል ተስፋፋ። ፭፻፸፬–፭፻፸፭ ም.ዓ. ገደማ።

[1] ነሆም እንዲህ ሆነ፣ ሌሂ ኢየሩሳሌ ምን ለቆ ከወጣ ሃምሳ አምስት ዓመ ታት አለፉ፤ ስለዚህ፣ ኔፊ፤ ለእኔ [a]ለያዕ ቆብ እነዚህ ነገሮች የተፃፉበትን [b]ትንሹን ሰሌዳ በተመለከተ [c]ትዕዛዝን ሰጠኝ።

[2] እናም እኔ ያዕቆብ፣ በጣም የከበሩ ናቸው ብዬ የማስባቸውን ጥቂት ነገሮች በእ ነዚህ ሰሌዳዎች ላይ እንድፅፍ፤ የኔፊ ህዝብ ተብለው ስለሚጠሩት ታሪክም ባጭሩ ካል ሆነ በስተቀር መፃፍ እንደሌለብኝም ትዕዛ ዝን ሰጠኝ።

[3] እርሱም የህዝቡን ታሪክ በሌላኛው የእ ርሱ ሰሌዳ ላይ መፃፍ እንዳለበት፣ እና እኔ እነዚህን ሰሌዳዎች ማቆየትና ለዘሮቼም፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፍ እን ዳለብኝ ተናግሯል።

[4] እናም ቅዱስ የሆነ ሰበካ፣ ወይም ታላቅ የሆነ ራዕይ፣ ወይም ትንቢት፣ ካለ በእነ ዚህ ሰሌዳዎች ላይ [d]ዋና ዋናዎቹን መቅ ረፅ፣ እስከተቻለም ድረስ ለክርስቶስ እና ለህዝባችን ስል መጻፍ አለብኝ።

[5] በእምነትና በታላቅ ጭንቀት የተነሳ ህዝባችንን በተመለከተ፣ ምን ነገሮች በእ ነርሱ ላይ [e]መሆን እንዳለባቸው በእውነት ለእኛ ተገልፆልናል።

[6] እናም ደግሞ እኛ ብዙ ራዕይና ብዙ የት ንቢት መንፈስ ነበረን፣ ስለዚህ [f]ስለክርስ ቶስ እና ስለሚመጣው መንግስቱም እና ውቅ ነበር።

[7] ስለሆነም የእስራኤል ልጆች [g]በምድ ረበዳው በነበሩበት ወቅት በፈተናው ጊዜ [h]በአመጽ እንደነበሩ ወደ እረፍቱ [i]እንዳ ይገቡ በማንኛውም መንገድ ቢሆን በቁጣው እንዳይምል፣ ህዝቦቻችን ወደ [j]እረፍ ቱም ይገቡ ዘንድ ወደ ክርስቶስ [k]እንዲ መጡ እናም የእግዚአብሔርን በጎነት እን ዲካፈሉ እናሳምናቸው ዘንድ በትጋት ሠራን።

[8] ስለዚህ፣ ሰዎች ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ [l]ለቁጣ የሚቀሰቅሰውን አመፅ [m]እንዳያ ምፁ፣ ነገር ግን ሰዎች ሁሉ በክርስቶስ እን ዲያምኑና፣ ሞቱን ይገነዘቡ ዘንድ፣ እናም [n]የመስቀሉን ስቃይና የዓለምን መሳለቅ ይቀበሉ ዘንድ ለማሳመን እንድንችል የእ ግዚአብሔርን እርዳታ እንፈልጋለን፤ ስለ ሆነም፣ እኔ ያዕቆብ፣ የወንድሜ ኔፊን ትዕ ዛዛት ለመፈፀም ኃላፊነቱን ወሰድኩ።

[9] እንግዲህ ኔፊ መሸምገል ጀመረ፣ እናም በቅርቡ [o]እንደሚሞት ተገነዘበ፤ ስለዚህ፣

---

[a] ፩ ፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. ያዕቆብ፣ የሌሂ ልጅ።
ለ ፪ ኔፊ ፭፡፳፯–፴፫፤ ያዕቆ. ፫፡፲፫–፲፭። ቅ.መ.መ. ሰሌዳዎች።
ሐ ያዕቆ. ፯፡፳፯።

[b] ፩ *ሀ* ይህም ከሌላ የሚልቅ፣ አስፈላጊ እቃዎች ማለት ነው።

[c] ፩ *ሀ* ፩ ኔፊ ፲፪።

[d] ፩ *ሀ* ፩ ኔፊ ፣፡፡–፣፩፤ ፣፣፪፡፳–፣፡።

[e] ፩ *ሀ* ዘኍል. ፳፯፡፳፭፤ ፩ ኔፊ ፣፣፯፡፣ ፳፣–፳፩።
ለ ዕብ. ፣፡፡፳።
ሐ ዘኍል. ፣፡፡፣ ፳፣፡፣ ዘዳግ. ፩፡፴፩–፴፣፤ ት. እና ቃ. ፹፡፡፡፣ ፳፣–፳፭።
መ ቅ.መ.መ. እረፍት።
ሠ ፪ ኔፊ ፪፡፴፩፤ ኦምኒ ፩፡፳፣፣፤ ሞሮኒ ፣፡፴፪።

[f] ፩ *ሀ* ፩ ኔፊ ፣፣፡፤ ፴፤
አልማ ፣፪፡፴፣–፴፣፤ ሔሌ. ፣፡፣፡።
ለ ቅ.መ.መ. አመጽ።
ሐ ጆ.ስ.ት. ማቴ. ፣፣፡፤ ፳፭–፳፣ (ተጨማሪ)፤ ሉቃ. ፣፡፡፡፣ ፳፣፡።

[g] ፩ *ሀ* ፪ ኔፊ ፩፡፣፡፡፤ ፣፡፡–፣፡፡።

[h] ፩ *ሀ* ፩ ኔፊ ፣፡–፣፩፤ ፣፪፡፡–፣፡፡።

[i] ፩ *ሀ* ዘኍል. ፳፣፡፣ ፳፣፡፣ ፩ ኔፊ ፣፣፡፣ ፣፡–፣፡፡።
ለ ዕብ. ፣፡፡፣ ፳፡።
ሐ ዘኍል. ፣፡፡፣ ፳፣፡፣ ዘዳግ. ፩፡፴፩–፴፣፤ ት. እና ቃ. ፹፡፡፡፣ ፳፣–፳፭።
መ ቅ.መ.መ. እረፍት።
ሠ ፪ ኔፊ ፪፡፴፩፤ ኦምኒ ፩፡፳፣፣፤ ሞሮኒ ፣፡፴፪።

[j] ፩ *ሀ* ፪ ኔፊ ፣፡፡፣ ፣፡፡–፣፡፡።

[k] ፩ *ሀ* ፪ ኔፊ ፣፡–፣፩፤ ፣፣፪፡፳–፣፡።

[l] ፩ *ሀ* ፪ ኔፊ ፣፡–፣፩፤ ፣፣፪፡፳–፣፡።

[m] ፩ *ሀ* ፪ ኔፊ ፣፡–፣፩፤ ፣፣፪፡፳–፣፡።

[n] ፩ *ሀ* ፪ ኔፊ ፣፡–፣፩፤ ፣፣፪፡፳–፣፡።

[o] ፩ *ሀ* ፪ ኔፊ ፣፡–፣፩፤ ፣፣፪፡፳–፣፡።

አንድ ሰው አሁን በህዝቡ ላይ ^ንጉሥና መሪ እንዲሆን፣ በመሣፍንቱ አገዛዝ መሰ ረት ሓቀባው።

፤ ህዝቡ ኔፌን እጅግ በመውደዱ፣ እር ሱም ለእነርሱ ታላቅ ጠባቂ በመሆኑ፣ የላ ባንንም ^ጎራዴ ለእነርሱ ለመከላከያ በመ ጠቀሙ፣ እናም ለደህንነታቸው በጊዜው ሁሉ በመስራቱ—

፤፩ ስለሆነም፣ ህዝቡ ስሙን በማስታወስ ለመቆየት ፈለጉ። እናም በነገስታት አገዛዝ መሠረት በእርሱ ምትክ የሚነግሱት ሁሉ ሁለተኛው ኔፌ፣ ሶስተኛው ኔፌና፣ ወዘተ ተብለው በህዝቡ ተሰየሙ፤ እናም ስማቸው ምንም ቢሆን፣ በህዝቡ እንዲህም ተሰየሙ።

፤፪ እናም እንዲህ ሆነ፣ ኔፌ ሞተ።

፤፫ አሁን ^ላማናውያን ያልነበሩት ህዝቦች ኔፋውያን ነበሩ፤ ይሁን እንጂ፣ ^ኔፋው ያን፣ ያዕቆባውያን፣ ዮሴፋውያን፣ ^ዞራማ ውያን፣ ላማናውያን፣ ልሙኤላውያን እና እስማኤላውያን ተብለው ይጠሩ ነበር።

፤፬ ነገር ግን፣ እኔ ያዕቆብ፣ ከእንግዲህ በኋላ እነርሱን በዚህ ስም አልለያቸውም፣ ነገር ግን የኔፌን ህዝቦች ለማጥፋት የሞ ከሩትን፣ ላማናውያን፣ ብዬ ^እጠራቸ ዋለሁ፣ እናም በነገስት አገዛዝ መሰረት፣ ለኔፌ ወዳጅ የሆኑትን፣ ^ኔፋውያን፣ ወይም ^የኔፌ ህዝብ፣ ብዬ እጠራቸዋለሁ።

፤፭ እናም አሁን እንዲህ ሆነ የኔፌ ህዝብ፣ በሁለተኛው ንጉስ የንግሥ ዘመን ልባቸውን ማደንደን ጀመሩ፣ እናም በጥቂቱ እራሳ ቸውን እንደ ጥንቱ ዳዊት እንዲሁም እንደ ልጁ ሰለሞን ብዙ ^ሚስቶችና ዕቁባቶችን በማድረግ በክፉ ልማድ የእራሳቸውን ፍላ ጎት ማሟላት ጀመሩ።

፤፮ አዎን፣ እናም ደግሞ እነርሱ ብዙ ወርቅና ብር መፈለግ ጀመሩ፣ እናም በኩ ራት እራሳቸውን ከፍ ማድረግ ጀመሩ።

፤፯ ስለዚህ፣ እኔ ያዕቆብ፣ መጀመሪያ ^መልእክቴን ከጌታ ካገኘሁ በኋላ ^በቤ ተመቅደስ ውስጥ ሳስተምራቸው እነዚህን ቃላት ሰጠኋቸው።

፤፰ እኔ ያዕቆብ፣ እናም ወንድሜ ዮሴፍ፣ ለዚህ ህዝብ ካህናትና መምህራን እንድን ሆን በኔፌ እጅ ^ተቀብተን ነበር።

፤፱ እናም ኃላፊነቱንም በመውሰድ፣ የእ ግዚአብሔርን ቃል በሙሉ ትጋት ካላስተ ማርናቸው የህዝቡን ኃጢኣት በራሳችን ላይ በመቀበል ^ኃላፊነታችንን ለጌታ ^አኃላን፤ ስለሆነም፣ ^ደማቸው ልብሳችንን እንዳይ በክል ባለን ኃይል ሰራን፤ አለበለዚያ ደማ ቸው ልብሳችንን ይበክላልና፣ እናም በመ ጨረሻው ቀን እንከን የለሽ ሆነን አንገኝም።

ምዕራፍ ፪

ያዕቆብ የሀብትን ፍቅር፣ ኩራትና፣ ምን ዝርናን አወገዘ—ሰዎች ወገናቸውን ለመ ርዳት ሀብትን ሊሹ ይችላሉ—ጌታ ከኔ ፋውያን መካከል ማንኛውም ሰው ከአንድ በላይ ሚስት እንዳይኖረው አዘዘ—ጌታ በሴቶች ንፁህነት ይደሰታል። ከ፳፻፸፬–፳፻፸፭ ም.ዓ. ገደማ።

፩ የኔፌ ወንድም ያዕቆብ፣ ኔፌ ከሞተ በኋላ ለኔፌ ህዝብ የተናገራቸው ቃላት—

፪ አሁን፣ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ፣ እኔ ያዕቆብ እግዚአብሔር በሰጠኝ ሀላፊነት መሰረት፣ ሀላፊነቴን በጥሞና ለመወጣት፣ እናም ኃጢአታችሁንም ከመጎናፀፊያዬ

፤ለ ፪ ኔፌ ፤፯፡፪፣ ጂረም ፩፡፲። ሐ ቅ.መ.መ. መቀባት።
፤ሀ ፩ ኔፌ ፡፡፡፣ ፪ ኔፌ ፡፡፡፣ ቃላት ፩፡ ፤፲፣ ሞዛያ ፩፡ ፤፲፯፣ ት.እና ቃ. ፤፲፯፡ ፩።
፤፲ ሀ ኢኖስ ፩፡ ፤፲፣ ት.እና ቃ. ፫፡ ፤፲፰።
ለ ቅ.መ.መ. ኔፋውያን።
ሐ ፩ ኔፌ ፡፣ ፴፩፣ ፡ ኔፌ ፩፡ ፴፯–፴፯።
፤፲፡ ሀ ሞዛያ ፳፭፡ ፤፪፣ አልማ ፪፡ ፤፩።
ለ ፪ ኔፌ ፡፣ ፤፩።
ሐ ፪ ኔፌ ፩፡ ፡፡
፤፲፩ ሀ ት.እና ቃ. ፲፴፪፡ ፴፰–፴፡፡
፤፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. ጥሪ፣ በእግዚአብሔር መጠራት፣ የተጠራበት።
ለ ፪ ኔፌ ፩፡ ፤፲፯።
ቅ.መ.መ. ቤተመቅደስ፣ የጌታ ቤት።
፤፲፰ ሀ ፪ ኔፌ ፩፡ ፳፯።
፤፡፡ ሀ ት.እና ቃ. ፲፯፡ ፣፡፡–፪።
ቅ.መ.መ. መጋቢ፣ መጋቢነት።
ለ ቅ.መ.መ. ሀላፊነት፣ ሀላፊ።
ሐ ፪ ኔፌ ፡፡፡፣ ፴፡፡።

አራግፍ ዘንድ፣ የእግዚአብሔርንም ቃል ለእናንተ አውጅ ዘንድ በዚህ ቀን ወደ ቤተ መቅደስ መጣሁ።

፫ እናም እስከዚህ ጊዜ ድረስ በተጠራሁ በት ኃላፊነት ትጉህ እንደነበርኩ እናንተም ታውቃላችሁ፤ ነገር ግን ባሁኑ ጊዜ ከዚህ ቀደም ከነበረኝ ይልቅ ለነፍሳችሁ ደህን ነት ከፍተኛ ስሜትና ስጋት ተከፍቼአለሁ።

፬ እነሆም፣ እስከዚህ ጊዜ ድረስ እኔ በሰ ጠኋችሁ፣ በጌታ ቃል ታዛዦች ነበራችሁ።

፭ ነገር ግን እነሆ፣ እኔን አድምጡኝ፣ እናም ከሁሉም በላይ ሀይለኛ በሆነው የሰማ ይና የምድር ፈጣሪ ድጋፍ "ሀሳባችንን በተ መለከተ ልናገራችሁ እንደምችል፣ እንዴ ትስ ኃጢያትን መስራት እንደጀመራችሁ፣ ለእኔም በጣም የረከሰ እንደሆነ፣ አዎን፣ ለእግዚአብሔርም የረከሰ እንደሆነ እወቁ።

፮ አዎን፣ ነፍሴን ያሳዝናል እናም የልባ ችሁን ክፋት በተመለከተ መመስከር ስላለ ብኝ፣ በፈጣሪዬ ፊት በእፍረት እንድሸማ ቀቅ ያደርገኛል።

፯ እናም ደግሞ እናንተን በተመለከተ፣ የብዙዎቹም ስሜት በእግዚአብሔር ፊት፣ ለእግዚአብሔርም አስደሳች በሆኑት፣ እጅግ ለስላሳና "ንፁህ፣ በቀላሉ ሊጎዱ በሚችል፣ በሚስቶቻችሁ እናም በልጆቻ ችሁ ፊት ^በኃይል መናገር ስላለብኝ አዝ ናለሁ፤

፰ እናም እነርሱ አስደሳቹን "የእግዚአብ ሔርን ቃል፣ አዎን፣ የቆሰለውን ነፍስ የሚ ፈውሰው ቃል ለመስማት ወደዚህ እንዲ መጡ እገምታለሁ።

፱ ስለሆነም፣ እንደወንጀላችሁ እናንተን ለመገሰፅ፣ የቆሰሉትን ቁስላቸው ለመዳ ንና ለመፈወስ ሳይሆን እንዲሰፋ ለማድ ረግ፤ እናም ያልቆሰሉት ደግሞ አስደሳቹን የእግዚአብሔር ቃል ከመጋበዝ ይልቅ ነፍ ሳቸውን ለመውጋት እናም በቀላሉ ሊጎዳ የሚችል አዕምሮአቸውን ለማቁሰል ከእ ግዚአብሔር በተቀበልሁት ጥብቅ ትዕዛዝ ምክንያትም በመገደዴ ነፍሴን ተጨቁኛል።

፲ ነገር ግን ስራው ታላቅ ቢሆንም፣ በእ ግዚአብሔር ጥብቅ "ትዕዛዝ መሰረት ማድ ረግ፣ እናም በልበ ንፁህና፣ በተሰበረ ልብ ፊት፣ እናም ሁሉን በሚገዛ አምላክ ^በሚ ቃኘው ዐይን ፊት ስለበደላችሁና ስለእር ኩሰታችሁ መናገር አለብኝ።

፲፩ ስለሆነም፣ እንደእግዚአብሔር ቃል "ግልፅነት እውነቱን ልነግራችሁ ይገባል። እነሆም ጌታን ስጠይቅ፣ ቃሉ እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ፥ ያዕቆብ ነገ ወደ ቤተ መቅ ደሱ ሂድ፣ እናም ለዚህ ህዝብ የምሰጥህን ቃል አውጅ።

፲፪ እናም አሁን እነሆ፣ ወንድሞቼ፣ ለእ ናንተ የማውጀው ቃል ይህ ነው፣ ብዙዎቻ ችሁ ወርቅና፣ ብር፣ እንዲሁም ለእናንተና ለዘሮቻችሁ "የቃል ኪዳን ምድር በሆነችው በዚህች ምድር ውስጥ በይበልጥ የያዘች ውን ሁሉንም ዓይነት የከበረ ^ብረት መፈ ለግ ጀምራችኋል።

፲፫ እናም የአምላክ እጅ በሰፊው ባርኳ ችኋል፣ ብዙ ሀብትንም አግኝታችኋል፤ አንዳንዶቻችሁም ከወንድሞቻችሁ በበ ለጠ ስለተቀበላችሁ በልባችሁ ኩራት "ከፍ ብላችኋል፣ እናም በለበሳችሁትም ልብስ ውድነት አንገታችሁን አደንድናችኋል፣ ራሳችሁንም ከፍ አድርጋችኋል፣ እናም ራሳችሁን ከወንድሞቻችሁ የተሻላችሁ ስለሚመስላችሁ እነርሱን አሳዳችኋቸዋል።

፲፬ እናም አሁን፣ ወንድሞቼ፣ እግዚአ ብሔር በዚህ ነገር ከበደል ነጻ ያደርገናል ብላችሁ ትገምታላችሁን? እነሆ፣ አይሆ ንም እላችኋለሁ። ነገር ግን እርሱ ይፈር ድባችኋል፣ እናም እናንተ በእነዚህ ነገሮች

፪ ፭ *ሀ* አልማ ፲፪፡፫፤ ት. እና ቃ. ፮፡ ፲፯። ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ።

፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. በጎነት።

ለ ት. እና ቃ. ፲፭፩፡ ፵፫።

፰ *ሀ* አልማ ፴፩፡ ፭።

፲ *ሀ* ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ትእዛዛት።

ለ ፪ ኔፊ ፱፡ ፵፬።

፲፩ *ሀ* ፪ ኔፊ ፳፭፡ ፱፣ ፴፩፡ ፪–፫።

፲፪ *ሀ* ፩ ኔፊ ፪፡ ፳።

ቅ.መ.መ. የቃል ኪዳን ምድር።

ለ ፩ ኔፊ ፲፰፡ ፳፫፣ ሔለ. ፮፡ ፱–፲፩፣ ኤተር ፲፡ ፳፫።

፲፫ *ሀ* ሞር. ፰፡ ፴፭–፴፱።

የምትቀጥሉ ከሆነ ፍርዱ በፍጥነት ይመ
ጣባችኋል።
፲፭ አቤቱ መውጋት እንደሚችል፣ እናም
በቅፅበት ዐይኑ ቅኝት ወደ አፈር ሊመታ
ችሁ እንደሚችል ቢያሳያችሁ!
፲፮ አቤቱ ከክፋትና ከእርኩሰት ነፃ ቢያ
ደርጋችሁ። እናም፣ አቤቱ የትዕዛዙን ቃል
ብትሰሙና፣ ይህ የልባችሁ ክፋት ነፍሳች
ሁን [ሀ]እንዲያጠፋ ባትፈቅዱ!
፲፯ ወንድሞቻችሁ እንደ እራሳችሁ አስ
ቡአቸው፣ እናም እነርሱም ልክ እንደ እና
ንተ [ለ]ሀብታም ይሆኑ ዘንድ፣ ከሁሉም ጋር
ተገናኚ እናም [ሐ]በንብረታችሁ ነፃ ሁኑ።
፲፰ ነገር ግን [መ]ሀብትን ከመፈለጋችሁ
በፊት፣ የእግዚአብሔርን [ሠ]መንግስት
ፈልጉ።
፲፱ እናም በክርስቶስ ተስፋን ካገኛችሁ
በኋላ፣ የምትፈልጉአቸው ከሆነ ሀብትን
ታገኛላችሁ፤ እነዚህንም [ረ]መልካም ለማ
ድረግ ዓላማ—የተራቆቱትን ለማልበስ፣
የተራቡትንም ለመመገብ፣ ምርኮኞችንም
ነፃ ለማውጣት፣ እናም ለታመሙና ለተሰ
ቃዩ ፋታን ለመስጠት ትፈልጓቸዋላችሁ።
፳ እናም አሁን፣ ወንድሞቼ፣ ኩራትን
በሚመለከት ተናግሬአችኋለሁ፤ እናም
እግዚአብሔር በሰጣችሁ ነገሮች የተነሳ
በልባችሁ ኩራት ጎረቤቶቻችሁን ያሰቃያ
ችሁ፣ እንዲሁም ያሳደዳችሁ ስለዚህ ምን
ትላላችሁ?
፳፩ እንዲህ አይነት ነገሮች ስጋን ሁሉ
ለፈጠረው የረከሱ ናቸው ብላችሁ አታስ
ቡምን? እናም አንዱ ፍጡር እንደሌላው
በፊቱ የከበረ ነው። ሁሉም ስጋም ከአፈር
ነው፤ እናም [ሀ]ትዕዛዛቱን ይጠብቁና እር
ሱን ለዘለዓለም ያከብሩት ዘንድ ለተመሳ
ሳይ ዓላማ ፈጥሯቸዋል።
፳፪ እናም አሁን ይህን ኩራት በተመለ
ከተ ለእናንተ ንግግሬን አቆማለሁ። እናም
የከፋ ወንጀልን በተመለከተ ለእናንተ መና
ገር ባይኖርብኝ፣ ልቤ በእናንተ እጅግ ትደ
ሰት ነበር።
፳፫ ነገር ግን በከፋው ወንጀላችሁ የተነሳ
የእግዚአብሔር ቃል ከብዶኛል። እነሆም
ጌታ እንዲህ ይላል—ይህ ህዝብ በክፋት ቀስ
በቀስ ማደግ ይጀምራል፤ ቅዱሳት መጻሕ
ፍትንም አይረዱም፣ ምክንያቱም የዳዊ
ትንና ልጁ ሰለሞንን በተመለከተ በተፃፉት
ነገሮች የተነሳ ዝሙትን በመፈፀማቸው ለእ
ራሳቸው ምክንያትን ይፈልጋሉ።
፳፬ እነሆ፣ ዳዊትና [ሀ]ሰለሞን በእውነት
ብዙ [ለ]ሚስቶችና ዕቁባቶች ነበሩአቸው፣
ይህም በፊቴ የረከሰ ነበር ይላል ጌታ።
፳፭ ስለዚህ፣ ጌታ እንዲህ ይላል፣ ይህን
ህዝብ ለራሴ [ሐ]ፃድቅ ቅርንጫፍ ከዮሴፍ የወ
ገብ ፍሬ አስነሳ ዘንድ በኃያል ክንዴ ከኢየ
ሩሳሌም ምድር አውጥቼዋለሁ።
፳፮ ስለሆነም፣ እኔ ጌታ እግዚአብሔር
ይህ ህዝብ እንደ ጥንቶቹ እንዲያደርግ አይ
ፈቅድም።
፳፯ ስለሆነም፣ ወንድሞቼ እኔን ስሙኝ፣
እናም የጌታንም ቃል አድምጡ—በመካ
ከላችሁ [ሀ]ከአንድ ሚስት በቀር ሌላ አይ
ኑረው፤ እና ዕቁባቶች ምንም አይኑረው።
፳፰ እኔ ጌታ እግዚአብሔር በሴቶች [ለ]ንፅ
ህና እደሰታለሁና። እናም ማመንዘር በእኔ
ፊት የረከሰ ነው፤ ይላል የሰራዊት ጌታ።
፳፱ ስለሆነም፣ ይህ ህዝብ ትዕዛዛቴን
ይጠብቃል፣ ወይም ምድሪቱ በእነርሱ

፲፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. ኩራት።
፲፯ *ለ* ፬ ኔፊ ፩፡፫።
ሐ ቅ.መ.መ. ምፅዋት፣ የምፅዋት ስጦታ፣ በጎ ድርጊት።
፲፰ *ሀ* ፩ ነገሥ. ፫፡፲፩–፲፫፣ ማር. ፲፡፲፯–፳፯፣ ፪ ኔፊ ፳፯፡፴፣ ት.እና ቃ. ፮፡፲፯። ቅ.መ.መ. ሀብቶች።
ለ ሉቃ. ፲፪፡፳፪–፴፩።
፲፱ *ሀ* ሞዛያ ፬፡፳፯።
፳፩ *ሀ* ት.እና ቃ. ፲፩፡፳፣ አብር. ፫፡፳፭–፳፯።
፳፪ *ሀ* ፩ ነገሥ. ፲፩፡፩፣ ነህ. ፲፫፡፳፭–፳፯።
ለ ፩ ነገሥ. ፲፩፡፩–፫፣ ዕዝ. ፱፡፩–፪፣ ት.እና ቃ. ፲፴፪፡፴፣ ፴፰–፴፱።
፳፭ *ሀ* ዘፍጥ. ፴፱፡፳፪–፳፮፣ ዓም. ፭፡፲፭፣ ፪ ኔፊ ፫፡፭፣ አልማ ፳፯፡፴፯። ቅ.መ.መ. ሌሂ፣ የኔፊ አባት።
፳፯ *ሀ* ት.እና ቃ. ፴፪፡፳፪፣ ፴፱፡፲፯። ቅ.መ.መ. ጋብቻ፣ መጋባት።
፳፰ *ሀ* ቅ.መ.መ. ንጹህነት።

የተነሳ ᵐየተረገመች ትሁን ይላል የሰራ
ዊት ጌታ።
፴ እኔ ለራሴ ᵐዘርን ለማቆም ከፈለኩኝ፣
ህዝቤን አዛለሁ፤ አለበለዚያ እነርሱ እነ
ዚህን ነገሮች ያዳምጣሉ ይላል የሰራዊት
ጌታ።
፴፩ እነሆ እኔ ጌታ በኢየሩሳሌም ምድር
ውስጥ፣ አዎን፣ እናም በህዝቤ ምድር
ሁሉ፣ በባሎቻቸው ክፋትና እርኩሰት የተ
ነሳ የህዝቤን ሴት ልጆች ሀዘንን ተመልክ
ቻለሁ፣ እናም ልቅሶአቸውን ሰምቻለሁ።
፴፪ እናም የሰራዊት ጌታ፣ ከኢየሩሳሌም
ምድር እንዲወጡ ያደረኩአቸው፣ የዚህ
ህዝብ መልካም ሴት ልጆች ጩኸት ወደ
እኔ በህዝቤ ወንዶች ላይ ይመጣ ዘንድ አል
ፈቅድም ይላል የሰራዊት ጌታ።
፴፫ በከባድ እርግማን፣ እንዲሁም ለጥ
ፋታቸውም፣ ካልጎበኘኋቸው በቀር የህዝቤ
ሴት ልጆች በሩህሩህነታቸው የተነሳ በምርኮ
አይወሰዱም፤ ምክንያቱም እነርሱ ᵐዝሙ
ትን እንደጥንቶቹ አይፈፅሙም ይላል የሰ
ራዊት ጌታ።
፴፬ እናም አሁን እነሆ፣ ወንድሞቼ፣ እነ
ዚህ ትዕዛዛት ለአባታችን ሌሂ ተሰጥተውት
እንደነበር ታውቃላችሁ፤ ስለሆነም በፊትም
ታውቋቸዋላችሁ፤ እናም ማድረግ የማይ
ገባችሁን እነዚህን ነገሮች በማድረጋችሁ
ለታላቅ እርግማን መጥታችኋል።
፴፭ እነሆ፣ ከወንድሞቻችን ከላማናው
ያን የበለጠ ᵐበደል ሰርታችኋል። በእነር
ሱም ፊት መጥፎ ምሳሌዎች በመሆናችሁ፣
የሩህሩህ ሚስቶቻችሁን ልብም ሰብራች
ኋል፣ የልጆቻችሁንም መተማመን አጥታ
ችኋል፤ እናም በልባቸው ጥልቅ ሀዘን በእ
ናንተ ላይ ወደ እግዚአብሔር መጥተዋል።
እናም በእናንተ ላይ በሚወርደው በእግዚ
አብሔር ቃል ጥብቅነት የተነሳ፣ ብዙ ልቦች
በሀዘን ቆሰሉ በጥልቅ ቁስልም ተበሱ።

ምዕራፍ ፫

በልባቸው ንፁህ የሆኑ የሚያስደስተውን የእግዚአብሔርን ቃል ይቀበላሉ—የላ ማናውያን ፅድቅ ከኔፋውያን ይል ቃል—ያዕቆብ ሳያገቡ ስለሚያመነዝሩ፣ ስለዝሙትና ስለማንኛውም ኃጢያት አሰ ጠነቀቀ። ከ፳፪ የ፴፭ ዓ.ዓ. ገደማ።

፩ ነገር ግን እነሆ፣ እኔ ያዕቆብ፣ በልባችሁ
ንፁህ ለሆናችሁ እናገራለሁ። በአዕምሮ ፅኑ
ነት ወደ እግዚአብሔር ተመልከቱ፣ በታላቅ
እምነትም ወደእርሱ ፀልዩ፣ እርሱም በመ
ከራችሁ ያፅናናችኋል፣ እናም ምክንያታች
ሁን ይማፀናል፣ ጥፋታችሁንም ለሚመኙ
ፍርድን ይልካል።
፪ አቤቱ በልባችሁ ንፁህ የሆናችሁ ሁሉ፣
ራሳችሁን አቅኑና አስደሳቹን የእግዚአብ
ሔርን ቃል ተቀበሉ፣ እናም ፍቅሩንም
ተቋደሱ፤ አዕምሮአችሁ ᵐፅኑ ከሆነ፣ ይህን
ለዘለአለም ለማድረግ ትችላላችሁና።
፫ ነገር ግን፣ እናንተ በልባችሁ ንፁህ ያል
ሆናችሁ በዚህ ቀን በእግዚአብሔር ፊት
ᵐየቆሸሻችሁ ወዮ፣ ወዮላችሁ፤ ንስሀ ካል
ገባችሁ ምድሪቱ በእናንተ ምክንያት የተ
ረገመች ትሆናለችና፤ እናም ላማናውያን
እንደ እናንተ ባይቆሽሹም፣ ይሁን እንጂ
በከባድ እርግማን ᵃተረግመዋል፣ እስከም
ትጠፉም እንኳን ይጎዱአችኋል።
፬ እናም እናንተ ንስሀ ካልገባችሁ፣ የር
ስት ምድራችሁን እነርሱ የሚወርሱበት ጊዜ
በፍጥነት ይመጣል፣ እናም ጌታ እግዚአ
ብሔር ፃድቃንን ከመካከላችሁ ᵐያወጣል።
፭ እነሆ፣ የእናንተ ወንድሞች፣ በቆሻሻ
ነታቸውና በቆዳቸው ላይ በመጣው እር
ግማን የተነሳ የጠላችኋቸው ላማናውያን፣
ከእናንተ የበለጠ ፃድቃን ናቸው፤ ምክን
ያቱም እነርሱ አንድ ሚስት ብቻ እንዲኖ
ራቸው እናም ምንም ዕቁባት እንዳይኖራ

፴፩ *ሀ* ኤተር ፪፡ ፴–፲፪።
፴፪ *ሀ* ሚል. ፪፡ ፲፫፣
ት. እና ቃ. ፲፴፪፡ ፴፩–፴፯።
፴፫ *ሀ* ቅ.መ.መ. ስሜታዊነ፣
ስሜታዊነት፣
በወሲብ የስነ ምግባር
ጉድለት።
፴፭ *ሀ* ያዕቆ. ፫፡ ፭–፯።
፫ ፪ *ሀ* አልማ ፶፯፡ ፴፯–፴፯።
፫ *ሀ* ቅ.መ.መ. እድፍ፣
እድፍነት።
ለ ፩ ኔፊ ፲፪፡ ፴፫።
፬ *ሀ* ኦምኒ ፩፡ ፭–፯፣ ፲፪–፲፫።

ቸው፣ እናም በመካከላቸውም ዝሙት እን ዳይፈጸም ዘንድ ለአባታችን የተሰጠውን የጌታን ትዕዛዝ ᵐአልረሱምና።

፲፮ እናም አሁን፣ ይህንን ትዕዛዝ ለመጠበቅ ይጥራሉ፤ ስለሆነም፣ ይህንን ትዕዛዝ ለመ ጠበቅ ጥረት የተነሳ ጌታ እግዚአብሔር እነ ርሱን አያጠፋም፣ ነገር ግን ለእነርሱ ᵐመሀሪ ይሆናል፤ እናም አንድ ቀን የተባረኩ ህዝ ቦች ይሆናሉ።

፲፯ እነሆ፣ ባሎቻቸው ሚስቶቻቸውን ᵐይወዳሉ፣ ሚስቶቻቸውም ባሎቻቸውን ይወዳሉ፤ እናም ባሎቻቸውና ሚስቶቻ ቸው ልጆቻቸውን ይወዳሉ፤ እንዲሁም የእነርሱ አለማመንና ወደ እናንተ ያላቸው ጥላቻ በአባቶቻቸው ክፋት የተነሳ ነው፤ ስለሆነም፣ በታላቁ ፈጣሪያችሁ አመለካ ከት እናንተ ምን ያህል ከእነርሱ የተሻላ ችሁ ናችሁ?

፲፰ ወንድሞቼ ሆይ፣ ከእነርሱ ጋር በእግ ዚአብሔር ዙፋን ፊት ስትቀርቡ እናንተ ለኃጢአታችሁ ንስሀ ካልገባችሁ የእነርሱ ቆዳ ከእናንተ የበለጠ ይነጣል በማለት እፈ ራለሁ።

፲፱ ስለሆነም፣ የእግዚአብሔር ቃል የሆነ ትዕዛዝ እሰጣችኋለሁ፣ ቆዳቸው በመጥቆሩ ምክንያት ከእንግዲህ አትሰድቧቸውም፤ በመቆሸሻቸውም ምክንያት አትሰድቧቸ ውም፤ ነገር ግን የራሳችሁን መቆሸሽ ታስ ታውሳላችሁ፣ እናም የእነርሱ መቆሸሽ የመጣው በአባቶቻቸው የተነሳ መሆኑን አስታውሱ።

፲ ስለሆነም፣ በፊታቸው ባስቀመጣች ሁት ምሳሌም የተነሳ ᵐየልጆቻችሁን ልብ እንዴት እንዳሳዘናችሁ ታስታውሳላችሁ፤ እናም ደግሞ በመቆሸሻችሁ የተነሳ፣ ልጆ ቻችሁን ወደ ጥፋት ታመጣላችሁ፣ እናም በመጨረሻው ቀን ኃጢአታቸው በራሳችሁ ላይ ይቆለላሉ።

፲፩ ወንድሞቼ ሆይ፣ ቃሌን አድምጡ፤ የነፍሳችሁን ስሜት አነቃቁ፤ ከሞት እንቅ ልፍ ትነቁ ዘንድ ራሳችሁን ᵐነቅንቁ፤ እናም የዲያብሎስ ᵃመልዕክተኛ በመሆን የሁለ ተኛው ᵇሞት ከሆነው እሳትና ዲን ራሳች ሁን እንዳትጥሉ ᶜከሲያል ህመም ራሳች ሁን ፍቱ።

፲፪ እናም አሁን እኔ ያዕቆብ፣ የሚያስ ከትሉትን ክፉ ነገሮች በመንገር ᵐከዝሙ ትና ᵃከአመንዝራነት፣ እንዲሁም ከማን ኛውም አይነት ኃጢያት እነርሱን በማስ ጠንቀቅ ለኔፊ ህዝብ ብዙ ነገሮችን ተና ገርኳቸው።

፲፫ እናም አሁን ቁጥራቸው ታላቅ እየ ሆኑ የመጡት የዚህ ህዝብ ነገር አንድ መቶኛ ክፍል ድርጊቶችም ᵐበእነዚህ ሰሌ ዳዎች ሊፃፍ አይቻልም፤ ነገር ግን አብዛ ኛው ድርጊታቸውና፣ ጦርነታቸው፣ እናም ፀባቸው፣ እንዲሁም የነገስታቶቻቸው የን ግስ ታሪክ በትልቁ ሰሌዳ ላይ ተፅፈዋል።

፲፬ እነዚህ ሰሌዳዎች የያዕቆብ ሰሌዳዎች ይባላሉ፣ እናም የተሰሩት በኔፊ እጅ ነው። እናም እነዚህን ቃላት መናገሬን አቆማ ለሁ።

ምዕራፍ ፩

ነቢያት ሁሉ አብን በክርስቶስ ስም አመ ለኩ—የአብርሃም ይስሃቅን ለመሰ ዋት ማቅረቡ የእግዚአብሔርና የአንድያ ልጁ አምሳል ነበር—በኃጢያት ክፍያው ሰዎች እራሳቸውን ከእግዚአብሔር ጋር ማስታረቅ አለባቸው—አይሁዶች የመ ሰረቱን ድንጋይ አይቀበሉም። ከ፳፻፴፬–፴፻፳፭ ም.ዓ. ገደማ።

፩ አሁን እነሆ፣ እንዲህ ሆነ እኔ ያዕቆብ፣ ለህዝቤ በቃሌ ብዙ በማስተማሬ (እናም የእ ኛን ቃላት በሰሌዳዎቼ ላይ ለመቅረፅ ባለው

፭ *ሀ* ያዕቆ. ፪፡፴፭።
፮ *ሀ* ፪ ኔፊ ፡፫፣ ፮–፯፣ ሔለ. ፲፭፡፲–፲፫።
፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. ቤተሰብ፣ ፍቅር።
፲ *ሀ* ቅ.መ.መ. ልጅ፣ ልጆች።
፲፩ *ሀ* አልማ ፭፡፮–፱።
ለ ፪ ኔፊ ፱፡፰–፱።
ሐ ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ሞት።
መ ቅ.መ.መ. ሲያል።
፲፪ *ሀ* ቅ.መ.መ. ዝሙት መፈጸም።
ለ ቅ.መ.መ. ምኞት፣ ክፉ፣ ክፋት።
፲፫ *ሀ* ፩ ኔፊ ፲፱፡፩–፪፣ ያዕቆ. ፩፡፩–፪።

ዲሁም ከእግዚአብሔርና ᵐከአንድያ ልጁ ጋር አምሳልነት ያለው፣ ለአብርሃም በምድ ረበዳ ልጁን ይስሀቅን ለመስዋዕት በማቅረብ ለእግዚአብሔር ትዕዛዝ ታዛዥ ሆኖ እንደተ ቆጠረለት፣ ለዚህም ምክንያት ይህም ለፅ ድቅ ለእኛ ተቀድሷል።

፲ ስለሆነም፣ እኛ ነቢያትን እንመረምራ ለን፣ እናም ብዙ ራዕይና ᵐየትንቢት መን ፈስ አለን፤ እነዚህ ሁሉ ᵃምስክሮች ስላሉ ንም ተስፋን እናገኛለን፣ እናም እምነታ ችን የማይናወጥ ሆኖ በእውነት በኢየሱስ ᵃስም ᵐስንገስፅ ያም ዛፉ፣ ወይንም ተራ ራው ወይም የባህሩ ሞገድ ይታዘዝልናል።

፲፩ ይሁን እንጂ፣ በፀጋው እናም ለሰው ልጆች እራሱን ዝቅ በማድረጉ እነዚህን ነገሮች የማድረግ ኃይል እንዳለን እናውቅ ዘንድ ጌታ እግዚአብሔር ᵐድክመታችንን ያሳየናል።

፲፪ እነሆ፣ የጌታ ስራ ታላቅና ድንቅ ነው። የእርሱ ᵐሚስጥር ጥልቀት እንዴት ᵃየማይ መረመር ነው፤ እናም ሰው የእርሱን መን ገድ ሁሉ ፈልጎ ለማወቅ የማይቻል ነው። እናም ለእርሱ ካልተገለፀለት በቀር ማንም ሰው የእርሱን ᵃመንገድ ᵐአያውቅም፤ ስለሆነም፣ ወንድሞች፣ የእግዚአብሔርን ራዕይ አትናቁ።

፲፫ እነሆም፣ ᵐሰው ᵃበቃሉ ኃይል ወደ ምድር ፊት መጥቷል፣ ምድርም በቃሉ ኃይል ተፈጥራለች። ስለሆነም፣ እግዚአ ብሔር መናገር ከቻለና፣ እንዲሁም ዓለም ከተፈጠረ፣ እና እርሱ ሲናገር ሰው ከተፈ ጠረ፣ አቤቱ ᵃምድርን ወይም በዚህ ፊት

፤ ፤ ᵐ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ።
ᵃ ሉቃ. ፳፬፡፳፭–፳፯፤ ያዕቆ. ፲፡፲፩፤ ሞዛያ ፲፫፡፴፫–፴፭፤ ት. እና ቃ. ፳፡፳፲፯።
፲ ᵐ ሙሴ ፲፡፲።
ᵃ ፤ ኔፊ ፳፲፡፳፬፤ ጄረም ፩፡፲፩፤ ሞዛያ ፲፫፡፳፯፣ ፴፣ አልማ ፳፲፡፲፩–፲፯። ቅ.መ.መ. የሙሴ ህግ።
ᵃ ገላ. ፣ ፡፳፬።
ᵐ ዘፍጥ. ፳፪፡፩–፲፬፤ ዮሐ. ፣ ፡፲፯–፲፳። ቅ.መ.መ. አንድያ ልጅ።
፲ ᵐ ቅ.መ.መ. ትንቢት፣ መተንበይ።
ᵃ ቅ.መ.መ. ምስክር።
ᵃ የሐዋ. ፣ ፡፭–፲፯፤ ፣ ፡፭ ፡፳፡፩።
ᵐ ቅ.መ.መ. ሀይል።
፲ ᵐ ኤተር ፲፪፡፳፯።
፲ ᵐ ት. እና ቃ. ፲፱፡፣ ፳፯፡፲፣ ፲፱፡፲፩።
ᵃ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ሚስጥሮች።
ᵃ ሮሜ ፲፩፡፴፣ ፴፣–፴፯።
ᵃ ኢሳ. ፶፭፡፭–፱።
ᵐ ፩ ቆሮ. ፪፡፱–፲፣ አልማ ፳፣ ፳፩–፳፪። ቅ.መ.መ. እውቀት።
፲ ᵐ ቅ.መ.መ. መፍጠር፣ ፍጥረት፣ ሰው፣ ሰዎች።
ᵃ ሞር. ፱፡፲፣ ሙሴ ፩፡፴፪።
ᵃ ሔለ. ፲፪፡፭–፲፣።

ያለው የእጁ ስራ እንደርሱ ፈቃድና ደስታ ማዘዝ አይችልምን?

፲ ስለሆነም፣ ወንድሞቼ፣ ከእጁ ᵐምክርን ለመቀበል እንጂ ጌታን ለመምከር አትሞክሩ። እነሆም፣ እናንተም ᵃበጥበብና፣ በፍርድ፣ እናም በታላቅ ምህረት፣ በስራው ላይ ሁሉ እንደሚመክር ታውቃላችሁ።

፲፩ ስለሆነም፣ የተወደዳችሁ ወንድሞች፣ እናም በክርስቶስ ባለው የትንሳኤ ኃይል መሰረት፣ ᵐትንሳኤን ታገኙ ዘንድ፣ እናም እምነት በማግኘትና እራሱን በስጋ ከመግለጡ በፊት መልካም የሆነውን የክብሩን ተስፋ በማግኘት ለእግዚአብሔር የክርስቶስ ᵃየመጀመሪያው ፍሬ ሆናችሁ ትቀርቡ ዘንድ ᵇበአንድያ ልጁ፣ በክርስቶስ ᶜየኃጢያት ክፍያ ከእርሱ ታረቁ።

፲፪ እናም አሁን፣ የተወደዳችሁ፣ እነዚህን ነገሮች ስነግራችሁ አትገረሙ፤ እናም የእርሱን ፍጹም እውቀት ለማወቅና፣ የትንሳኤንና የሚመጣው ዓለም እውቀትን ለማግኘት የክርስቶስን የኃጢያት ክፍያ ለምን ᵐአትናገሩም?

፲፫ እነሆ፣ ወንድሞቼ፣ ትንቢትን የሚናገር ሰዎች እንዲረዱት ዘንድ ትንቢት ይናገር፤ ᵐመንፈስ እውነቱን ይናገራል እንጂ አይዋሽምና። ስለሆነም፣ እርሱ ነገሮች በእርግጥ ᵃእንዳሉ፣ እናም ነገሮች በእርግጥ እንደሚሆኑ ይናገራል፤ ስለሆነም፣ እነዚህ ነገሮች ለነፍሳችን ደህንነት ᵇበግልፅ ተገልጠውልናል። ነገር ግን እነሆ፣ በእነዚህ ነገሮች እኛ ብቻ ምስክር አይደለንም፤ እግዚአብሔር ደግሞ ለጥንቶቹ ነቢያት ተናግሯቸዋልና።

፲፬ ነገር ግን እነሆ፣ አይሁዶች ᵐአንገተ ደንዳና ህዝቦች ነበሩ፣ እናም ግልፁን ቃላት ᵃንቀዋል፣ ነቢያትን ገድለዋልም፣ መረዳት የማይችሉትን ነገሮች ተመኝተዋልም። ስለሆነም፣ ᵇበመታወራቸው ምክንያት፣ እውርነቱም የሚመጣው ከሚገባው በላይ በማተኮር ነው፤ እነርሱ ይወድቁ ዘንድ አስፈላጊ ነው፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ግልፅነቱን ከእነርሱ ወስዷልና፣ እናም ስለ ፈለጉት ᶜየማይረዱትን ብዙ ነገሮች ሰጥቷቸዋል። እናም እነርሱ ስለፈለጉት እግዚአብሔር አድርጎታል፣ ይህም እነርሱ ይሰና ከሉበት ዘንድ ነው።

፲፭ እናም አሁን እኔ ያዕቆብ፣ ለመተንበይ በመንፈስ ተመርቻለሁ፤ በአይሁድ ᵐመሰናከልም፣ በእርሱም ላይ የሚገነቡትን እንዲሁም የደህንነት መሰረት የሚያገኙበትን ᵃአለቱን ᵇእንደማይቀበሉ በእኔ ባለው የመንፈስ ስራ ተረድቻለሁ።

፲፮ ነገር ግን እነሆ፣ እንደ ቅዱሳን መጽሐፍት መሰረት፣ ይህ አይሁዶች የሚገነቡበት ᵐአለት፣ ታላቅና የመጨረሻና፣ በብቻ የተረጋገጠ ᵃመሰረት ይሆናል።

፲፯ እናም አሁን፣ ወዳጆቼ፣ እርግጠኛውን መሰረት ከካዱ በኋላ፣ የማዕዘን ራስ ይሆን ዘንድ በእርሱ ላይ ለመመስረት እነርሱ እነዚህን ᵐእንዴት ማድረግ ይቻላቸዋል?

፲፰ እነሆ፣ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ፣ በምንም መንገድ ከመንፈሴ ፅኑነት ከተነቃነቅኩኝ እና ስለእናንተ ባለኝ ጭንቀት ምክንያት ካልተሰናከልኩኝ፣ ይህን ሚስጥር ለእናንተ እገልጥላችኋለሁ።

፲ ሀ ፪ ኔፊ ፱፡ ፳፰–፳፱፤ አልማ ፴፯፡ ፲፪፣ ፴፯፣ ት. እና ቃ. ፫፡ ፬፣ ፲፫።
ለ ቅ.መ.መ. ሁሉን የሚያውቅ፣ ጥበብ።
፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
ለ ሞዛያ ፲፭፡ ፳፩–፳፫፣ ፲፡ ፱፤ አልማ ፵፡ ፲፯–፳፩።
ሐ ዕብ. ፭፡ ፱።
መ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ።
፲፪ ሀ ፪ ኔፊ ፳፭፡ ፳፯።
፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ፣ እውነት።
ለ ት. እና ቃ. ፶፫፡ ፳፬።
ሐ አልማ ፲፫፡ ፳፫።
፲፬ ሀ ማቴ. ፳፫፡ ፴፯–፴፰፣ ፪ ኔፊ ፳፭፡ ፪።
ለ ፪ ቆሮ. ፲፩፡ ፫፣ ፩ ኔፊ ፲፱፡ ፯፣ ፪ ኔፊ ፴፫፡ ፪።
ሐ ኢሳ. ፶፬፡ ፲፯፣ ሮሜ ፲፩፡ ፳፭።
መ ፪ ኔፊ ፳፭፡ ፩–፪።
፲፭ ሀ ኢሳ. ፳፡ ፲፫–፲፭፣ ፩ ቆሮ. ፩፡ ፳፫፣ ፪ ኔፊ ፲፳፡ ፲፫–፲፭።
ለ ቅ.መ.መ. አለት፣ የማዕዘን ድንጋይ።
ሐ ፩ ኔፊ ፲፡ ፲፩።
፲፮ ሀ መዝ. ፻፲፰፡ ፳፪–፳፫።
ለ ኢሳ. ፳፰፡ ፲፮፣ ሔለ. ፭፡ ፲፪።
፲፯ ሀ ማቴ. ፲፱፡ ፴፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡ ፴።

ምዕራፍ ፮

ያዕቆብ ከዜኖስ ስለለማው እና ስለዱር የወይራ ዛፍ ታሪክ ጠቀሰ—እነርሱም ከእስራኤልና ከአህዛብ ጋር የተመሳሰሉ ናቸው—የእስራኤል መበተን እና መሰባሰብ ቀድሞ ተጠቅሷል—ስለኔፋውያንና ላማናውያን እንዲሁም ስለእስራኤል ቤት ሁሉ ተጠቅሷል—አህዛብ ከእስራኤል ጋር ይዳቀላሉ—በመጨረሻም የወይኑ ስፍራ ይቃጠላል። ከ፮፲፱–፸፭ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እነሆ፣ ወንድሞቼ፣ እንዲህ ሲል ለእ
ስራኤል ቤት የተናገረውን የነቢዩ [ሀ]ዜኖስን
ቃል ማንበባችሁን አታስታውሱምን፤
፪ የእስራኤል ቤት ሆይ አድምጡኝ፣
እናም የእኔ የጌታ ነቢይን ቃል ስሙ።
፫ እነሆም፣ ጌታ እንዲህ ይላል፥ [ለ]የእስ
ራኤል ቤት ሆይ፣ እኔ እናንተን አንድ ሰው
ወስዶ [ሐ]በወይኑ ስፍራ ከሚንከባከበው፣
ከለማው [መ]የወይራ ዛፍ ጋር አመሳስላች
ኋለሁ፤ እናም አደገ፣ አርጅቶ [ሠ]መበስበ
ስም ጀምረ።
፬ እናም እንዲህ ሆነ በወይኑ ስፍራ ባለቤቱ
ሄዶ፣ የወይራው ዛፍ መበስበስ እንደ ጀመረ
ተመለከተም፤ እናም እንዲህ አለ—ምና
ልባት ለጋና ለምለም ቅርንጫፎችን ያበ
ቅል ዘንድና፣ እንዳይጠፉም እኔ እመለ
ምለዋለሁ፣ እቆፍረዋለሁ፣ እናም እንከ
ባከበዋለሁ።
፭ እናም እንዲህ ሆነ እንደቃሉ መለመ
ለው፣ ቆፈረውም፣ ተንከባከበውም።
፮ እናም እንዲህ ሆነ ከብዙ ቀናት በኋላ
ትናንሽና ጥቂት ለጋና ለምለም ቅርንጫ
ፎችን ማውጣት ጀመረ፤ ነገር ግን እነሆ፣
ከዋናው ጫፍ ያለው መሞት ጀመረ።
፯ እናም እንዲህ ሆነ የወይኑ ስፍራ ባለቤት
ተመለከተው፣ እናም ለአገልጋዩ እንዲህ
ሲል ተናገረው—ይህንን ዛፍ ማጣት ያሳ
ዝነኛል፤ ስለሆነም፣ ሂድና [ሁ]ከየዱር ወይራ
ዛፍ ቅርንጫፉን ልቀም፣ ወደ እኔም አም
ጣው፤ እናም እኛ መጠውለግ የጀመሩትን
ዋና ዋና ቅርንጫፎች እንነቅላለን፣ ይቃ
ጠሉም ዘንድ ወደ እሳቱ እንጥላቸዋለን።
፰ እናም እነሆ፣ የወይኑ ስፍራ ጌታ እን
ዲህ ይላል፥ ከእነዚህ ለጋና ለምለም ቅርን
ጫፎች ብዙዎቹን እወስዳለሁ፣ እናም በም
ፈልገው ቦታ አዳቅላቸዋለሁ፤ እናም የዚህ
ዛፍ ስር የሚጠፋም ከሆነ ምንም አይደለም፣
ፍሬውን ለራሴ አስቀምጣለሁ፤ ስለሆነም፣
እነዚህን ለጋና ለምለም ቅርንጫፎች እወ
ስዳለሁ፣ እናም በፈለግሁበት ቦታ አዳቅ
ላቸዋለሁ።
፱ አንተ የዱር የወይራ ዛፍ ቅርንጫፎችን
ውሰድና፣ በእነዚያም [ሀ]ምትክ አዳቅላቸው፤
እናም የወይኑን ስፍራዬን እንዳያበላሹት
ዘንድ፣ እኔ የመለመልኳቸውን ወደ እሳቱ
እጥላቸዋለሁ፣ እናም አቃጥላቸዋለሁ።
፲ እናም እንዲህ ሆነ የወይኑ ስፍራ ጌታ
አገልጋይ እንደወይኑ ስፍራ ጌታ ቃል አደ
ረገ፣ እናም [ለ]በዱሩ የወይራ ዛፍ ቅርንጫ
ፎችን አዳቀለ።
፲፩ እናም የወይኑ ስፍራ ጌታ እንዲቆፍ
ርና እንዲመለምል፣ እናም እንዲንከባከ
በው ለአገልጋዩ እንዲህ አለው—ይህንን ዛፍ
ማጣት ያሳዝነኛል፣ ስለሆነም፣ ምናልባት
እንዳይጠፉ ስሮቹን ለማዳን እችል ዘንድ፣
ለእኔ ለራሴ እነርሱን አስቀር ዘንድ ይህን
ነገር አድርጌአለሁ።
፲፪ ስለሆነም፣ መንገድህን ሂድ፣ ዛፉን
ጠብቅ፣ እናም በቃሌ መሰረት ተንከባከ
በው።
፲፫ እናም ይህን ራቅ ባለው በወይን አት
ክልት ስፍራዬ፣ በምፈልገው በማንኛ
ውም ቦታ፣ [ሐ]አስቀምጠዋለሁ፣ ይህም አን
ተን አያሳስብህም፤ እናም ይህን የማደር
ገው የተፈጥሮ ቅርንጫፎቹን ለራሴ አድን

፩ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. ዚኖስ።
፫ ሀ ሕዝ. ፴፮፡ ፳።
ለ ቅ.መ.መ. እስራኤል።
ሐ ት. እና ቃ. ፲፩፡ ፶፬።
መ ቅ.መ.መ. የጌታ የወይን አትክልት ስፍራ።
ሠ ሮሜ ፲፩፡ ፲፯–፳፬።
ሠ ቅ.መ.መ. የወይራ ዛፍ።
ሠ ሮሜ ፲፩፡ ፲፯፣ ፳፬።
ሁ ሮሜ ፩፡ ፲፫።
ለ ሀ ቅ.መ.መ. አህዛቦች።
፲፫ ሀ ፩ ኔፊ ፲፡ ፲፪።

ዘንድ፣ እናም ደግሞ ለራሴ ፍሬውን ለማከ
ማቸት ነው፤ ምክንያቱም ይህን ዛፍና ፍሬ
ውን ማጣት ያሳዝነኛል።

፲፬ እናም እንዲህ ሆነ የወይኑ ስፍራ ጌታ
መንገዱን ሄደ፣ እናም ተፈጥሮአዊውን የለ
ማውን የወይራ ዛፍ ቅርንጫፎች ራቅ ባለው
የወይን ስፍራ፤ እንደፈቃዱና ደስታው አን
ዳንዱን በአንድ፣ እናም አንዳንዱን በሌላ
ቦታ ደበቀው።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ ረጅም ጊዜ አለፈ፣
የወይኑ ስፍራ ጌታም ለአገልጋዩ እንዲህ
አለው—ና ወደ ወይኑም ስፍራ እንሰራ
ዘንድ እንሂድ።

፲፮ እናም እንዲህ ሆነ የወይኑ ስፍራ ጌታና
ደግሞ አገልጋዩ ወደ ወይኑ ስፍራ ለመስራት
ሄዱ። እናም እንዲህ ሆነ አገልጋዩ ለጌታው
እንዲህ አለው፥ እነሆ፣ በዚህ ተመልከት፣
ዛፉን ተመልከት።

፲፯ እናም እንዲህ ሆነ የወይኑ ስፍራ ጌታ
የዱር የወይራው ቅርንጫፎች የተዳቀሉበ
ትን ዛፍ አየም ተመለከተም፤ እናም ዛፉ
ማበብና ᵐፍሬ ማፍራት ጀመሯል። እርሱም
መልካም እንደሆነ አየ፤ እናም ፍሬው እን
ደተፈጥሮው ፍሬ ነበር።

፲፰ እናም ለአገልጋዩ እንዲህ አለው፥
እነሆ፣ የዱር ቅርንጫፎቹ የዛፉን ስር እር
ጥበት ወስደውታል፣ ስለዚህ ስሩም የበ
ለጠ ጥንካሬን አግኝቷል፤ እናም የእዚያ
ስር ብዙ ጥንካሬ ስለነበረው የዱር ቅርንጫ
ፎች የለሙ ፍሬዎች አፍርተዋል። አሁን፣
እነዚህን ቅርንጫፎች ባናዳቅላቸው ኖሮ
ዛፉ ይሞት ነበር። እናም አሁን፣ እነሆ፣
ዛፉ ያፈራቸውን ፍሬ አከማቻለሁ፤ እናም
ለወቅቱም ፍሬውን ለራሴ አከማቻለሁ።

፲፱ እናም እንዲህ ሆነ የወይኑ ስፍራ ጌታ
ለአገልጋዩ እንዲህ አለው፥ ና ራቅ ወዳ
ለው የወይኑ ስፍራ እንሂድ፣ እናም ፍሬ
ውን ለራሴ በወቅቱ አከማቸው ዘንድ፣ የተ
ፈጥሮው ቅርንጫፍ ብዙ ፍሬ ደግሞ እንዳ
ላመጣ እንመልከት።

፳ እናም እንዲህ ሆነ ባለቤቱ የተፈጥሮ
ቅርንጫፎቹን ወደ ደበቀበት ስፍራ ሄዱ፣
እናም እርሱ ለአገልጋዩ፥ እነዚህን ተመል
ከት አለው፤ ᵐየመጀመሪያው ብዙ ፍሬ እን
ደሚያስገኝም ተመለከተ፤ እናም መልካም
እንደሆነ ደግሞ ተመለከተ። ለአገልጋዩም
እንዲህ አለው፥ ፍሬውን ውሰድና ለራሴ
አስቀምጠው ዘንድ ለወቅቱ አከማቸው፤
እነሆም፣ ለረጅም ጊዜ ተንከባክቤዋለሁ፣
እናም ብዙ ፍሬን አስገኝቷል።

፳፩ እናም እንዲህ ሆነ አገልጋዩ ለጌታው
አለው፥ ይህንን ዛፍ ወይም የዛፉን ቅርን
ጫፍ ለመትከል እዚህ ለምን መጣህ? እነ
ሆም ከወይኑ ስፍራ ሁሉ ያልለማ ነበርና።

፳፪ እናም የወይኑ ስፍራ ጌታም አለው፥
እኔን አትምከረኝ፤ መጥፎ የመሬት ቦታ
እንደነበረ አውቃለሁ፤ ስለሆነም፣ እንዲ
ህም ብዬሃለሁ፣ ይህን ለረጅም ጊዜ ተንከ
ባክቤዋለሁ፣ እናም ብዙ ፍሬን እንዳስገኘ
ተመልክተሃል።

፳፫ እናም እንዲህ ሆነ የወይኑ ስፍራ ጌታ
ለአገልጋዩ እንዲህ አለው፥ እዚህ ተመል
ከት፤ እነሆ ሌላ የዛፉን ቅርንጫፍ ደግሞ
ተክያለሁ፤ እናም አንተ ይህ መሬት ከመ
ጀመሪያው የበለጠ መጥፎ መሆኑን ታው
ቃለህ። ነገር ግን ዛፉን ተመልከት። ለረጅም
ጊዜ ተንከባክቤዋለሁ፣ እናም ብዙ ፍሬን
አስገኝቷል፤ ስለዚህ፣ ሰብስበውና ለራሴ
አስቀምጠው ዘንድ ለወቅቱ አከማቸው።

፳፬ እናም እንዲህ ሆነ የወይኑ ስፍራ ጌታ
ለአገልጋዩ በድጋሚ አለው፥ ወደዚህ ተመ
ልከት፣ እናም እኔ የተከልኩትን ሌላ ᵐቅር
ንጫፍ ደግሞ ተመልከት፤ እነሆ እኔ ደግሞ
ተንከባክቤዋለሁ፣ ይህም ፍሬን አስገኝ
ቷል።

፳፭ እናም ለአገልጋዩ አለው—ወደዚህ
ተመልከት፣ እናም የመጨረሻውን ተመ
ልከት። እነሆ፣ ይህን ᵐበመልካሙ መሬት
ቦታ ላይ ተክየዋለሁ፣ ለዚህ ለረጅም ጊዜም
ተንከባክቤዋለሁ፣ እናም የለማውን ፍሬ

፲፯ ᵐ ዮሐ. ፲፭ ፥ ፲፮።
፳ ᵐ ያዕቆ. ፭ ፥ ፴፱።
፳፩ ᵐ ሕዝ. ፲፯ ፥ ፳፪–፳፩ ፤ አልማ ፲፯ ፥ ፲፯ ፤
ᵐ ኔፊ ፲፭ ፥ ፳፩–፳፩።
፳፭ ᵐ ᵐ ኔፊ ፪ ፥ ፳።

በግማሹ ክፍል ብቻ አስገኝቷል፤ ለሌላው የዛፉ ክፍልም የዱር ፍሬ አፍርቷል፣ እነሆ ይህን ዛፍ እንደሌሎቹ ተንከባክቤዋለሁ።

፳፮ እናም እንዲህ ሆነ የወይን ስፍራው ጌታ ለአገልጋዩ አለ—መልካም ሀፍሬ የማያፈሩትን ቅርንጫፎች ንቀላቸውና ወደ እሳቱ ጣላቸው።

፳፯ ነገር ግን እነሆ፣ አገልጋዩም አለ—እንግረዘው፣ እንኮትኩተውም፣ እናም ለትንሽ ጊዜ እንንከባከበው፣ ምናልባት በወቅቱ የምታከማቸውን መልካም ፍሬን ያመጣልህ ይሆናል።

፳፰ እናም እንዲህ ሆነ የወይኑ ስፍራ ጌታና የወይን ስፍራው ጌታ አገልጋይ የአትክልቱን ስፍራ ፍሬዎች በሙሉ ተንከባከቡት።

፳፱ እናም እንዲህ ሆነ ረጅም ጊዜ አለፈ፣ እናም የወይኑ ስፍራ ጌታ ሀለአገልጋዩ እንዲህ አለው—ና፣ በወይኑ ስፍራ እንደገና እንስራ ዘንድ ወደ ወይኑ ስፍራ እንሂድ። እነሆም፣ ለቀኑ ቀርቧል፣ እናም ሐየመጨረሻው በፍጥነት ይመጣል፣ ስለሆነም፣ ለራሴ ለወቅቱ የሚሆን ፍሬ ማከማቸት አለብኝ።

፴ እናም እንዲህ ሆነ የወይኑ ስፍራ ጌታና አገልጋዩ ወደ ወይኑ ስፍራ ሄዱ፤ የተፈጥሮ ቅርንጫፎቹ ወደ ወደቁበትና፣ የዱር ቅርንጫፎቹ ወደተዳቀሉለት ዛፍም ሄዱ፣ እናም እነሆ ሁሉም ሀዓይነት ፍሬዎች ዛፉ እንዲያዘነብል አደረጉት።

፴፩ እናም እንዲህ ሆነ የወይን ስፍራው ጌታ ከፍሬው እያንዳንዱን አይነት፣ ከትንሽ እስከትልቅ፣ ቀመሰ። የወይኑ ስፍራ ጌታም እንዲህ አለ፤ እነሆ፣ ለረጅም ጊዜ ይህን ዛፍ ተንከባክበናል፣ እናም ለወቅቱ የሚሆን ብዙ ፍሬንም ለራሴ አከማችቻለሁ።

፴፪ ነገር ግን እነሆ፣ በዚህ ጊዜ ብዙ ፍሬን አስገኝቷል፣ እናም ከዚህ ውስጥ ሀምንም መልካም የሆነ የለም። እናም እነሆ፣ ከሁሉም ዓይነት መጥፎ ፍሬዎች አሉ፤ በብዛት ብንሰራበትም፣ ለእኔ ምንም ጥቅም አያስገኝልኝም፤ እናም አሁን ይህንን ዛፍ በማጣቴ አሳዝኖኛል።

፴፫ እናም የወይኑ ስፍራ ጌታ ለአገልጋዩ አለው—እኔ እንደገና መልካሙን ፍሬ ለራሴ አስቀምጥ ዘንድ በዛፉ ላይ ምን ማድረግ ይሻለናል?

፴፬ እናም አገልጋዩ ለጌታው አለው፥ እነሆ፣ እነርሱን ከዱሩ የወይራ ዛፍ ቅርንጫፎች ላይ ስላዳቀልክ ስሩን ተንከባክበዋል፣ ስለዚህ በህይወት ቆይተዋል እናም አልጠፉም፤ ስለሆነም፣ አሁንም አንተ መልካም መሆናቸውን ተመልክተሃል።

፴፭ እናም እንዲህ ሆነ የወይኑ ስፍራ ጌታ ለአገልጋዩ እንዲህ አለው፥ ዛፉ ለእኔ ምንም አይጠቀመኝም፣ እናም መጥፎ ፍሬን እስከሰጠ ድረስ ስሩም ምንም አይጠቀመኝም።

፴፮ ይሁን እንጂ፣ ስሩ መልካም እንደሆነ አውቃለሁና፣ ለራሴ ዓላማ እነርሱን አድኛለሁ፤ እናም እስከአሁን ባላቸው ጥንካሬም የተነሳ ከዱር ቅርንጫፎቹ መልካም ፍሬን ሰጡ።

፴፯ ነገር ግን እነሆ የዱር ቅርንጫፎቹ አደጉና፣ የዚያ ስሩ ሀሊሸከማቸው አልቻለም፤ እናም ስሩ የዱር ቅርንጫፎቹን መሸከም ስላቃተው እርሱ መጥፎ ፍሬን አፈራ፤ እርሱም ብዙ መጥፎ ፍሬዎችን በማፍራቱ መጥፋት እንደ ጀመረ ትመለከታለህ፤ እናም ስለዚህ እርሱን ለማዳን አንድ ነገር ካላደረግን ወደ እሳት እንዲጣል በፍጥነት ይበስላል።

፴፰ እናም እንዲህ ሆነ የወይኑ ስፍራ ጌታ ለአገልጋዩ አለው—ራቅ ወዳለው የወይኑ ስፍራ እንሂድና፣ የተፈጥሮ ቅርንጫፎቹም ደግሞ መጥፎ ፍሬን እንደሚያፈሩ እንመልከት።

፴፱ እናም እንዲህ ሆነ ራቅ ወዳለው ወደ

፳፭ ለ ፫ ኔፊ ፲፥፲፪–፲፫።
፳፮ ሀ ማቴ. ፯፥፲፭–፳፤
አልማ ፭፥፴፮፤
ት. እና ቃ. ፺፯፥፯።
፳፱ ሀ ት. እና ቃ. ፻፭፥፶፭፤
፻፫፥፳፬።
ለ ቅ.መ.መ. የመጨረሻ ቀናት፤
የኋለኛው ቀናት።
ሐ ፪ ኔፊ ፴፥፲፤
ያዕቆ. ፮፥፪።
፴ ሀ ቅ.መ.መ. ክህደት።
፴፪ ሀ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፲፱።
፴፯ ሀ ት. እና ቃ. ፵፭፥፳፰–፴።

ወይኑ ስፍራ ሄዱ። እናም እንዲህ ሆነ የተ
ፈጥሮ ቅርንጫፎቹ ፍሬ ደግሞ እንደተበሰ
በሰ ተመለከቱ፤ አዎን፣ [ሀ]የመጀመሪያውና
ሁለተኛው ደግሞ የመጨረሻውም፤ እናም
ሁሉም በስብሰዋል።

፯ እናም የመጨረሻው [ለ]የዱር ፍሬ መል
ካሙን ፍሬ ያፈራውን የዛፍ ክፍል አሸንፎ
ታል፣ እንዲሁም ቅርንጫፉ ጠውልጓልና
ሞቷል።

፰ እናም እንዲህ ሆነ የወይኑ ስፍራ ጌታ
አለቀሰ፣ እናም ለአገልጋዩ አለው፡ ለወ
ይኑ ስፍራዬ ከዚህ የበለጠ [ሐ]ምን ማድረግ
እችላለሁ?

፱ እነሆ፣ የወይኑ ስፍራ ፍሬ ከዚህ በስ
ተቀር ሁሉም እንደበሰበሱ አውቃለሁ።
እናም በአንድ ወቅት መልካም ፍሬን ያመ
ጣው ደግሞ አሁን በስብሷል፤ እናም አሁን
የወይኔ ስፍራ ዛፎች በሙሉ ያለመቆረጥና
ወደ እሳት ያለመጣል በስተቀር ለምንም
መልካም አይደሉም።

፲ እናም እነሆ ይህ የመጨረሻው የጠወ
ለገ ቅርንጫፍ፣ [ሀ]በመልካሙ መሬት ላይ
አዎን፣ ከሌላው ከወይን ስፍራዬ መሬት
ክፍሎች ሁሉ በላይ ምርጥ በሆነው ላይ እን
ኳን ነበር የተከልኩት።

፲፩ እናም ይህን ዛፍ በቦታው እተክል
ዘንድ ይህን ምድር [ለ]የሚያበላሹትንም
ደግሞ ሰቆርጥ ተመልክተሃል።

፲፪ እናም የዚህ ዛፍ ክፍል መልካም ፍሬን
ሲያፈራና፣ ከፊሉም የዱር ፍሬን ሲያፈራ
ተመልክተሃል፤ እናም ቅርንጫፎቹን መል
ምዬ ወደ እሳቱ ባለመጣሌ፣ እነሆ፣ እነርሱ
መልካሙን ቅርንጫፍ አሸንፈውት እንዲ
ጠወልግ አደረጉት።

፲፫ እናም አሁን፣ እነሆ፣ ለወይኑ ስፍራዬ
ሁሉንም አይነት ጥንቃቄ ብንወሰድም፣
በዚያ ያሉት ዛፎች በስብሰዋል፣ ስለዚህ
መልካም ፍሬን አልሰጡም፤ እናም እነዚ
ህን ለማዳን፣ የእነዚህን ፍሬዎች በወቅቱ
ለእኔ ለማከማቸት ተስፋ አድርጌ ነበር። ነገር
ግን፣ እነሆ፣ እነርሱ ልክ እንደዱር የወይራ
ዛፍ ሆነዋል፣ [ሀ]መቆረጥና ወደ እሳት የሚ
ጣሉ ከመሆን በስተቀር ምንም ዋጋ የሌላ
ቸው፤ እናም እነርሱን ማጣቴ አሳዝኖኛል።

፲፬ ነገር ግን በወይኑ ስፍራዬ ውስጥ ከዚህ
የበለጠ ምን ማድረግ እችላለሁ? እናም እን
ዳልንከባከብ እጄን ሰበሰብኩኝን? አይደ
ለም፣ ተንከባክቤዋለሁ፤ ኮትኩቼዋለሁ፤
እንዲሁም ከርክሜዋለሁ፤ ፍግም አፍስሻ
ለሁ፤ ቀኑን ሙሉ እጄን [ሀ]ዘርግቻለሁም፣
[ለ]መጨረሻው ተቃርቧልም። እናም የወይን
ስፍራዬን ዛፎች ሁሉ መቁረጤና፣ እንዲቃ
ጠሉ ወደ እሳቱ መጣሌ አሳዝኖኛል። የወ
ይን ስፍራዬን ያበላሸው ማን ነው?

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ አገልጋዩ ለጌታው
አለው—የወይኑ ስፍራህ ትልቅነት አይደ
ለም—በዚያ ያሉት ቅርንጫፎች መልካም
የሆኑትን ስሮች አላሸነፉምን? እናም ቅር
ንጫፎቹ ስሩን በማሸነፋቸው የተነሳ እነሆ
ጥንካሬን ለራሳቸው በማድረግ ከስሩ ጥን
ካሬ የበለጠ በፍጥነት አድገዋል። እነሆ፣
እላለሁ፣ የወይኑ ስፍራ ዛፍህ የተበላሸው
ለዚህ አይደለም እንዴ?

፲፮ እናም እንዲህ ሆነ የወይኑ ስፍራ ባለ
ቤት ለአገልጋዩ አለው፡ የወይን ስፍራ
መሬት እንዳያቆሽሽ እንሂድና የወይኑን
ስፍራ ዛፍ እንቁረጥ ወደ እሳት እንጣላቸ
ውም፣ የምችለውን ያህል አድርጌአለሁና።
ለወይኑ ስፍራዬ ከዚህ የበለጠ ምን ማድ
ረግ እችላለሁ?

፲፯ ነገር ግን እነሆ፣ አገልጋዩ ለወይኑ ስፍራ
ጌታ አለው—ለትንሽ [ሀ]ጊዜ አቆየው።

፲፰ እናም ጌታውም አለ፡ አዎን፣ ለትንሽ
ጊዜ እተወዋለሁ፣ ምክንያቱም የወይን ስፍ
ራዬን ዛፎች ማጣት ያሳዝነኛልና።

፲፱ ስለሆነም፣ ራቅ ባለው የወይኑ ስፍራዬ

ሀ፲፩ ሀ ያዕቆ. ፭፡፣ ፰፡፣ ፰፲፡ ፰፭።
ሀ ሞር. ፮፡፮–፲፰።
ሀ፲፩ ሀ ፪ ኔፊ ፰፮፡ ፰፱።
ሀ፲፫ ሀ ፪ ኔፊ ፭፡ ፮።
ሀ፲፭ ሀ ኤተር ፲፫፡ ፳–፳፩።
ሀ፲፮ ሀ ፫ ኔፊ ፳፮፡ ፲፩።
ሀ፲፯ ሀ ፪ ኔፊ ፳፰፡ ፴፪፣ ያዕቆ. ፮፡ ፱።
ለ ቅ.መ.መ. አለም—የአለም መጨረሻ።
፱ ሀ ያዕቆ. ፭፡ ፰፯።

የተከልኩትን የእነዚህን ᵐቅርንጫፎች እን ውሰድ፣ እናም ከመጡበት ዛፍ ላይ እናዳቅ ላቸው፣ እናም ፍሬያቸው መራራ ከሆኑት እነዚያ ቅርንጫፎች እንመልምል፣ እናም የዛፉ የተፈጥሮ ቅርንጫፎችን በምትኩ እና ዳቅል።

፶፫ እናም ይህን የማደርገው ዛፉ እንዳይ ጠፋና፣ ምናልባት ስሩን ለራሴ አላማ አድ ነው ዘንድ ነው።

፶፬ እናም እነሆ፣ በፈለኩበት ቦታ የተከል ኩት የተፈጥሮ ቅርንጫፍ ስሮች እስከአሁን በህይወት ናቸው፤ ስለሆነም፣ ለራሴ ዓላማ ደግሞ አድናቸው ዘንድ፣ ከዚህ ዛፍ ቅር ንጫፎችን እወስዳለሁ፣ እናም በተፈጥሮ ቅርንጫፉ ላይ ᵐአዳቅላቸዋለሁ። አዎን፣ ደግሞ ለራሴ ስሮቹን ለመጠበቅና፣ በብቁ ጠንካራ ሲሆኑ መልካም ፍሬ ወደእኔ እን ዲያመጡልኝ ዘንድ፣ እናም በወይኑ ስፍ ራዬ ፍሬም እደሰት ዘንድ የእናት ዛፋቸው ቅርንጫፎችን በእነርሱ ላይ አዳቅላለሁ።

፶፭ እናም እንዲህ ሆነ የዱር ከሆነው የተ ፈጥሮ ዛፉ ቅርንጫፎቹን ወሰዱ፣ እናም ደግሞም ዱር ወደሆነው ተፈጥሮአዊ በሆ ነው ዛፍ ላይ አዳቅሉት።

፶፮ እናም ደግሞ የዱር የሆነውን የተፈ ጥሮ ዛፍ ወሰዱ፣ በእናታቸው ዛፍ ላይም ተዳቀሉ።

፶፯ እናም የወይኑ ስፍራ ጌታ ለአገልጋዩ አለው፣ ከሁሉም በላይ መራራ ከሆኑት በስ ተቀር የዱር ቅርንጫፎቹን ከዛፎቹ ላይ አት መልምል፣ እናም በእነርሱም ላይ እኔ በተ ናገርኩት መሰረት አዳቅላቸው።

፶፰ እናም የወይኑን ስፍራ ዛፎች እንደገና እንንከባከባቸዋለን፣ ቅርንጫፎቹንም እን ከረክማለን፤ እናም ከዛፎቹ ውስጥ እነዚያን መጥፋት የሚገባቸውን የበሰሉትን ቅርንጫ ፎች እናለመልማለን፣ ወደ እሳትም እንጥ ላቸዋለን።

፶፱ እናም ይህን የማደርገው በመልካምነ ታቸው ምክንያት የዛፉ ስር ይጠነክራል ብዬ ነው፤ እናም በቅርንጫፎቹ መቀያየር የተነሳ መልካሙ መጥፎውን ያሸንፋል።

፷ እናም የተፈጥሮ ቅርንጫፎቹንና ስሩን በማዳኔና፣ የተፈጥሮ ቅርንጫፎቹን ወደ እናታቸው ዛፍም በድጋሚ በማዳቀሌና፣ የእናታቸው ዛፍን ስር በማዳኔ፣ ምናል ባት የወይኑ ስፍራዬ ዛፎች በድጋሚ መል ካም ᵐፍሬን ያስገኛሉ፤ እናም በወይኑ ስፍ ራዬም ፍሬ ድጋሚ ደስታን እንዳገኝና፣ ምናልባት የመጀመሪያውን ፍሬ ስሩንና ቅርንጫፎቹን በማዳኔ እጅግ ደስታ እን ዲሰማኝ—

፷፩ ስለሆነም፣ በወይኑ ስፍራ በምንችለው በትጋት ᵐእንድንሰራ፣ መንገዱን እንድና ዘጋጅ ሂድ፣ እናም ᶮአገልጋዮችን ጥራ፣ ከሌሎቹ ፍሬዎች ሁሉ በላይ መልካምና ድንቅ የሆነውን ተፈጥሮአዊውን ፍሬ እን ደገና አስገኛለሁ።

፷፪ ስለሆነም፣ በዚህ በመጨረሻው ጊዜ እንሂድና በምንችለው እንስራ፣ እነሆም መጨረሻው ተቃርቧልና፣ እናም ይህ የወ ይኑ ስፍራዬን የምመለምልበት የመጨረሻ ጊዜ ነው።

፷፫ ቅርንጫፎችን አዳቅል፤ እናም የመ ጀመሪያ ይሆኑ ዘንድ ᵐከመጨረሻዎቹ ጀምሩ፣ የመጀመሪያዎቹም የመጨረሻ ይሆኑ ዘንድ፣ ሁሉንም ለአንዴና ለመጨ ረሻ ጊዜ እንንከባከባቸው ዘንድ፣ ያረጁት ንና ወጣቶቹን፣ የመጀመሪያዎቹንና የመ ጨረሻዎቹን፣ እና የመጨረሻዎቹንና የመ ጀመሪያዎቹን፣ ዛፎቹን ኮትኩቷቸው።

፷፬ ስለዚህ፣ ቆፍሩአቸውና መልምሉ አቸው፣ እናም ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ፍግ አድርጉባቸው፣ ምክንያቱም መጨ ረሻው ቀርቧልና። እናም እነዚህ በመጨ ረሻ የተዳቀሉት ካደጉ፣ እንዲሁም የተፈ

ሺ፪ ሀ ቅ.መ.መ. እስራኤል—
የእስራኤል መሰብሰብ።
ሺ፩ ሀ ፩ ኔፊ ፲፭፡፲፪–፲፯።
ሺ ሀ ኢሳ. ፳፯፡፮።
ሺ፩ ሀ ት. እና ቃ. ፴፱፡፲፩፣ ፲፫፣
፲፯።
ለ ያዕቆ. ፮፡ ፪፣
ት. እና ቃ. ፳፬፡፲፱።
ሺ፫ ሀ ፩ ኔፊ ፲፫፡ ፣ ፣
ኤተር ፲፫፡ ፲–፲፪።

ጥሮ ፍሬን ካፈሩ፣ እነርሱም ያድጉ ዘንድ ለእነርሱ መንገድን ታዘጋጃላችሁ።

፰፩ እናም ማደግ ሲጀምሩ በመልካሙ ጥንካሬውና ባለው መጠን መሰረት መራራ ፍሬ የሚያፈሩትን ቅርንጫፎች ታስወግዳላችሁ፤ እናም ስሩ ለተዳቀሉት እጅግ ጠንካራ እንዳይሆንባቸው፣ እናም በእዚያ የተዳቀሉት እንዳይጠፉና፣ የወይኑ ስፍራዬን ዛፎች እንዳላጣ፣ መጥፎውንም ሁሉ በአንዴ [ሠ]አታስወግዱም።

፰፪ የወይኑ ስፍራ ዛፎቼን ማጣት ያሳዝነኛልና፤ ስለሆነም፣ ስሩና ቅርንጫፉ በጥንካሬ እኩል እንዲሆን፣ መልካሙ መጥፎውን እስኪያሸንፈው፣ እናም የወይኑ ስፍራዬን ቦታ አንዳያበላሹት መጥፎው ተቆርጦ ወደ እሳት እስከሚጣል ድረስ፣ መልካሙ በሚያድግበት መሰረት መጥፎውን ታስወግዳላችሁ፤ እና እንደዚህም መጥፎውን ከአትክልት ስፍራዬ ጠርጌ አስወግደዋለሁ።

፰፫ እናም የተፈጥሮውን ዛፍ ቅርንጫፎች በተፈጥሮው ዛፍ ላይ በድጋሚ አዳቅለዋለሁ፤

፰፬ እናም የተፈጥሮውን ዛፍ ቅርንጫፎች በዛፉ የተፈጥሮ ቅርንጫፎች ላይ አዳቅላለሁ፤ እና እንደዚህ ተፈጥሮአዊውን ፍሬ ያፈሩ እንዲሁም አንድ ይሆኑ ዘንድ በድጋሚ እነርሱን በአንድነት አመጣቸዋለሁ።

፰፭ እናም መጥፎው [ሀ]ይጣላል፣ አዎን፣ ከአትክልት ስፍራዬ መሬት ሁሉም እንኳን፤ እነሆም፣ ወይኑ ስፍራዬን ይህን አንዴ ብቻ እከረከመዋለሁ።

፰ እናም እንዲህ ሆነ የወይኑ ስፍራ ባለ ቤት [ለ]አገልጋዩን ላከ፤ እናም አገልጋዩ ሄደና ጌታው እንዳዘዘው አደረገ፣ ሌሎች አገልጋዮቹንም አመጣ፤ እናም እነርሱ [ሐ]ጥቂት ነበሩ።

፰፮ እናም የወይኑ ስፍራ ጌታ አላቸው፡ ሂዱና በአቅማችሁ በወይኑ ስፍራ [መ]ስሩ። እነሆም ይህ የወይኑን ስፍራዬን የምንከባ ከብበት [ሠ]የመጨረሻ ጊዜ ነው፤ መጨረሻው ቀርቦ ደርሷልና፣ ወቅቱም በፍጥነት ይመጣል፤ እናም በአቅማችሁ ከእኔ ጋር ከሰራችሁ በቅርቡ ለሚመጣው ጊዜ ለራሴ ባከማቸሁት ፍሬ [ረ]ደስታ ይኖራችኋል።

፰፯ እናም እንዲህ ሆነ አገልጋዮቹ ሄዱና በአቅማቸው ሰሩ፤ የወይኑ ስፍራ ጌታ ደግሞም ከእነርሱ ጋር ሰራ፤ እናም በሁሉም ነገሮች የወይኑን ስፍራ ጌታ ትዕዛዛት ተቀበሉ።

፰፰ እናም በወይኑ ስፍራ እንደገና የተፈጥሮ ፍሬ መሆን ጀመረ፣ እናም የተፈጥሮ ቅርንጫፎች ማደግና እጅግም መፋፋት ጀመሩ፤ የዱር ቅርንጫፎች መመልመልና መጣል ጀመሩም፤ እነርሱም ስራቸውና ጫፋቸው በጥንካሬው መሰረት እኩል እስኪሆኑ ጠበቁት።

፰፱ እናም መጥፎው ከወይኑ ስፍራ እስከሚጣልና ጌታው ዛፎቼ እንደገና የተፈጥሮ ፍሬ እንዲያፈሩ ለራሱ እስኪያድን ድረስ፣ በወይኑ ስፍራ ጌታ ትዕዛዛት መሰረት እንደዚህ በሙሉ ትጋት ሰሩ፤ እነርሱም እንደ [ሠ]አንድ አካል ሆኑ፤ ፍሬዎቹም እኩል ነበሩ፤ እናም የወይኑ ስፍራ ጌታ ከመጀመሪያው ጀምሮ ለእርሱ እጅግ ውድ የሆነውን የተፈጥሮ ፍሬ ለራሱ አድኗል።

፰፲ እናም እንዲህ ሆነ የወይኑ ስፍራ ጌታ ፍሬው መልካም መሆኑንና፣ የወይኑንም ስፍራ ከእንግዲህ እንዳልበሱበሱ ባየ ጊዜ አገልጋዮቹን ጠራቸውና እንዲህ አላቸው፥ እነሆ፣ ለመጨረሻ ጊዜ የወይኑን ስፍራዬን ተንከባክበናል፤ እንደ ፍቃዴ እንዳደረኩም ተመልክታችኋል፤ እናም የተፈጥሮ ፍሬን አድኜዋለሁ፣ ልክ መጀመሪያ እንደነበረም መልካም ነው። እናንተም [ሠ]የተባረካችሁ ናቸሁ፤ በወይኑ ስፍራዬ ከእኔ ጋር በትጋት በመስራታችሁ፣ ትዕዛዛቴንም በመጠበቃ

፰፩ ሠ ት. እና ቃ. ፹፮፡፮–፯።
፰፪ ሠ ፩ ኔፊ ፳፪፡፲–፲፯፣ ፳፫፣ ፪ ኔፊ ፴፡፣ ፬ ኔፊ ፴፡፡–፲።
፰ ሠ ት. እና ቃ. ፻፩፡፱፣ ፹፩፣ ፻፫፡፣ ፻፲፡፣ ፳፩።
ለ ፩ ኔፊ ፲፡፡፣ ፲፪።
፰፩ ሠ ማቴ. ፳፩፡፳፤ ያዕቆ. ፮፡፪–፣ ት. እና ቃ. ፴፣፡፣–፡።
ለ ት. እና ቃ. ፴፱፡፲፯፣ ፴፣፡፡–፲፡።
ሐ ት. እና ቃ. ፲፳፡፣–፲፯።
፰፱ ሠ ት. እና ቃ. ፴፯፡፳፤ ፰፲ ሠ ፩ ኔፊ ፲፣፡፣ ፴፯።

ችሁና፣ የወይኑ ስፍራዬ ከእንግዲህ እን ዳይበሰብስ፣ በድጋሚ ^ተፈጥሮአዊ ፍሬን በማምጣታችሁና፣ መጥፎው ስለተጣለ፣ እነሆ በወይን ስፍራዬ ፍሬ የተነሳ እናንተ ከእኔ ጋር ደስታ ይኖራችኋል።

፳፮ እነሆም *ለረጅም ጊዜ በፍጥነት ለሚመጣው ወቅት የወይኑን ስፍራዬን ፍሬ ለራሴ አከማቻለሁ፤ እናም ለመጨ ረሻ ጊዜ የወይኑን ስፍራዬን ተንከባከብ ኩት፣ ከረከምኩትም፣ እናም ኮተኮትኩት፣ ፍግም አደረግሁበት፤ ስለዚህ፣ በተናገር ኩት መሰረት ከፍሬው ለራሴ ለረጅም ጊዜ አከማቻለሁ።

፳፯ እናም መጥፎው ፍሬ በድጋሚ በወ ይኑ ስፍራዬ በሚወጣበት ጊዜ ጥሩውና መጥፎው እንዲሰበሰቡ አደርጋለሁ፤ እናም መልካሙን ለራሴ አስቀምጣለሁ፣ መጥፎ ውንም ወደ ራሱ ስፍራ እጥለዋለሁ። ከዚ ያም በኋላ *ወቅቱ እንዲሁም መጨረሻው ይመጣል፤ እናም የወይኑን ስፍራዬን በእ ሳት ^እንዲቃጠል አደርገዋለሁ።

ምዕራፍ ፯

ጌታ እስራኤልን በመጨረሻው ቀን ይሰበ ስባል — ዓለም በእሳት ትቃጠላለች — ከእ ሳቱ ባህርና ከዲኑ ለመዳን ሰዎች ክርስ ቶስን መከተል ይኖርባቸዋል። ከ፳፪–፴፪ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም አሁን፣ እነሆ፣ ወንድሞቼ እተ ነብያለሁ ብዬ ለእናንተ እንደተናገርኩት እነሆ፣ ትንቢቴ ይህ ነው—የእስራኤልን ቤት በተመለከተ ከለማው ወይራ ዛፍ ጋር በማመሳሰል ነቢዩ *ዜኖስ የተናገራቸው ነገ ሮች በእርግጥ ይሆናሉ።

፪ እናም በድጋሚ ለሁለተኛ ጊዜ ህዝቡን *ለማዳን እጁን የሚያነሳበት ቀን፣ አዎን፣ ለመጨረሻው ጊዜ እንኳን፣ የጌታ ^አገል ጋይ ወደፊት በመቀጠል ^በኃይሉ *የወ ይኑን ስፍራ *የሚንከባከብበትና፣ የሚ ከረክምበት ቀን ነው፤ እናም ከዚያ በኋላ ^መጨረሻው በፍጥነት ይመጣል።

፫ እናም በወይኑ ስፍራ በትጋት የሰሩት እንዴት የተባረኩ ናቸው፤ እናም ወደ ራሳ ቸው ስፍራስ የሚጣሉት እንዴት የተረገሙ ናቸው! እናም ዓለም በእሳት *ትቃጠላለች።

፬ እናም *የእስራኤልን ቤት ስሮችና ቅር ንጫፎች ያስታወሰው አምላካችን እንዴት መሀሪ ነው፤ እናም ለእነርሱ ቀኑን ሙሉ ^ክንዱን ይዘረጋል፤ እነርሱም ^አንገተ ደንዳና እና ተቃዋሚ ህዝብ ናቸው፤ ነገር ግን አብዛኞቹም ልባቸውን ባያጠጥሩ በእ ግዚአብሔር መንግስት ይድናሉ።

፭ ስለሆነም፣ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ፣ ንስሀ እንድትገቡም፣ በልባችሁም ሙሉ ዓላማ እንድትመጡና፣ እግዚአብሔር ለእናንተ *እንደፀና እናንተም እንድትፀኑ በጥሞና ቃላት እለምናችኋለሁ። እናም በቀን ብርሃን የምህረት ^ክንዱ ወደ እና ንተ በተዘረጋ ጊዜ ልባችሁን አታጠጥሩ።

፮ አዎን፣ ዛሬ፣ ድምፁን ብትሰሙ፣ ልባ ችሁን አታጠጥሩ፤ ለምንስ *ትሞታላችሁ?

፯ እነሆም፣ ቀኑን ሁሉ በመልካሙ የእ ግዚአብሔርን ቃል ከተመገባችሁ በኋላ፣ መጥፎ ፍሬን አፍርታችሁ *በመቆረጥ ወደ እሳት መጣል ይገባችኋልን?

፳፭ *ለ* ቅ.መ.መ. እስራኤል።
፳፮ *ሀ* ፩ ኔፊ ፳፪፡፡–፳፫፡፡
ቅ.መ.መ. አንድ ሺህ አመት።
፳፯ *ሀ* ራዕ. ፳፡፪–፲፡
ት. እና ቃ. ፳፱፡፡ ፳፪፡፡–፳፱፡
፶፫፡፡ ፳፱–፶፫፡
፲፫፡፡ ፲፣–፲፣፲፯።
ለ ቅ.መ.መ. አለም—የአለም
መጨረሻ።
፮ ፩ *ሀ* ያዕቆ. ፭፡፡ ፩።
፪ *ሀ* ፩ ኔፊ ፳፪፡፡ ፣–፣፪፡
ት. እና ቃ. ፲፣፡፡ ፣፩።
ቅ.መ.መ. የወንጌል ዳግም
መመለስ።
ለ ያዕቆ. ፭፡፡ ፡፡፩።
ሐ ፩ ኔፊ ፣፡፡ ፣፡፡።
መ ቅ.መ.መ. የጌታ የወይን
አትክልት ስፍራ።
ሠ ያዕቆ. ፭፡፡ ፡፡፩።
ረ ፪ ኔፊ ፡፡ ፣።
፫ *ሀ* ፪ ኔፊ ፳፯፡፡ ፪፡
ያዕቆ. ፭፡፡ ፡፡፯፡
ት. ኔፊ ፳፭፡፡ ፩።
፬ *ሀ* ፪ ሳሙ. ፣፡ ፳፡፡።
ለ ያዕቆ. ፭፡ ፶፣።
ሐ ሞዛያ ፣፫፡ ፳፬፡፡
፭ *ሀ* ቅ.መ.መ. አንድነት።
ለ አልማ ፭፡ ፡፣፫–፡፡፡፡
፫ ኔፊ ፬፡ ፣፡፡።
፣ *ሀ* ሕዝ. ፣፡፡፡ ፳፩–፳፫፡፡
፣ *ሀ* አልማ ፭፡ ፣፩–፣፪፡
፫ ኔፊ ፳፣፡ ፣፩–፣፪፡፡
፬ *ሀ* ፪ ሳሙ. ፣ ፡ ፳፡፡
ለ ያዕቆ. ፭ ፡ ፶፣ ፡
ሐ ሞዛያ ፣ ፡ ፳ ፡ ፡
፭ *ሀ* ቅ.መ.መ. አንድነት
ለ አልማ ፭ ፡ ፡ ፡–፡ ፡ ፡
፫ ኔፊ ፬ ፡ ፣ ፡ ፡
፣ *ሀ* ሕዝ. ፣ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡–፡ ፡ ፡
፣ *ሀ* አልማ ፭ ፡ ፣ ፩–፣ ፪ ፡
፫ ኔፊ ፳ ፣ ፡ ፣ ፩–፣ ፪ ፡ ፡

፳ እነሆ፣ እነዚህን ቃላት ትቃወማላች ሁን? የነቢያቱን ቃላትስ ትቃወማላችሁን፤ ስለእርሱ ብዙዎች ከተናገሩ ከተባለ በኋላ፣ ክርስቶስን በተመለከተስ የተነገሩትን ቃላት ሁሉ ትቃወማላችሁን፤ እናም የክርስቶስን መልካም ቃል፣ የእግዚአብሔርን ኃይልና፣ የመንፈስ ቅዱስን ᐪስጦታን ትክዳላችሁን፣ የቅዱስ መንፈስ እርካታንም ታጠፋላች ሁን፣ እናም ለእናንተ የተመሰረተውን ታላ ቁን የቤዛነት ዕቅድ ትሳለቁበታላችሁን?

፳፩ እነዚህን ነገሮች ካደረጋችሁ፣ በክ ርስቶስ ያለው የቤዛነትና የትንሳኤ ኃይል ᐪበእግዚአብሔር የፍርድ ወንበር ፊት በእ ፍረትና በመጥፎ ᐩጸጸት እንደሚያቆማችሁ አታውቁምን?

፲ እናም ᐪበፍርድ ኃይል መሰረት፣ ፍርድ ሊካድ አይችልምና፣ እናንተ በነበልባሉ ወደ ማይጠፋው፣ እናም ጢሱም ለዘለ ዓለም እስከዘለዓለም ወደሰማይ ወደሚ ወጣው፣ ᐩየእሳቱ ባህርና ዲን ᐧመጨረሻ የሌለው ᐪስቃይ ወደሆነው፣ የእሳት ባህ ርና ዲን መሄድ ይገባችኋል።

፲፩ እንግዲህ አቤቱ፣ የተወደዳችሁ ወን ድሞቼ፣ ንስሀ ግቡ፣ ᐪበጠባቡም ደጅ ግቡ፣ እናም ዘለዓለማዊ ህይወትን እስከምታገኙ ድረስ በቀጥተኛ ጎዳና ቀጥሉ።

፲፪ አቤቱ ᐪብልህ ሁኑ፤ ከዚህ የበለጠ ምን ማለት እችላለሁ?

፲፫ በመጨረሻም ኃጢአተኞችን ᐪበመ ጥፎ ስጋትና ፍርሃት በሚመታው በአስደ ሳቹ በእግዚአብሔር የፍርድ ወንበር ፊት እስከምንገናኝ ድረስ ደህና ሁኑ እላችኋ ለሁ። አሜን።

ምዕራፍ ፯

ሼረም ክርስቶስን ካደ፣ ከያዕቆብ ጋር ተጣላ፣ ምልክትን በግድ ፈለገ፣ እናም በእግዚአብሔር ተቀሰፈ—ሁሉም ነቢ ያት ስለክርስቶስና ስለኃጢያት ክፍያው ተናግረዋል—ኔፋውያን በዘመናቸው እን ደሚንከራተቱ፣ በመከራ እንደተወለዱና፣ በላማናውያን እንደተጠሉ ኖሩ። ከ፭፻፸፬–፬፻፸፭ ዓ.ዓ. ገደማ።

፩ እናም አሁን እንዲህ ሆነ ጥቂት አመ ታት ካለፉ በኋላ፣ ከኔፋውያን መካከል ሰሙም ሼረም የተባለ አንድ ሰው መጣ።

፪ እናም እንዲህ ሆነ እርሱ በህዝቡ መካ ከል መስበክና፣ ክርስቶስ የሚባል እንደሌ ለም ለእነርሱ ማወጅ ጀመረ። እናም ለህ ዝቡ ብዙ የሽንገላን ነገሮች ሰበከ፤ ይህን ንም ያደረገው የክርስቶስን ትምህርት ለመ ጣል ነበር።

፫ እናም የህዝቡንም ልብ ያስት ዘንድ በት ጋት በመስራት የብዙዎችን ልብ አሳተ፤ እናም እኔ ያዕቆብ በሚመጣው ክርስቶስ እምነት እንዳለኝ ስለሚያውቅ ወደ እኔ ይመጣ ዘንድ ብዙ አጋጣሚዎችን ፈለገ።

፬ እናም የተማረ ነበር፣ ስለዚህ የህዝቡን ቋንቋ በፍጹም እውቀት ያውቅ ነበር፣ ስለ ሆነም፣ በዲያብሎስ ኃይል መሰረት ብዙ ሽንገላንና፣ ብዙ የንግግር ኃይል መጠቀም ችሏል።

፭ እናም እነዚህን ነገሮች በተመለከተ ብዙ ᐪራዕይና ብዙ ነገሮችን ያየሁ ቢሆንም፣ እርሱ እኔን ከእምነቴ ለማናወጥ ተስፋ ነበ ረው፤ እኔ በእውነት መላዕክቶችን አይቻ ለሁ፣ እነርሱም እኔን አስተምረውኛልና። እናም ደግሞ ከጊዜ ወደጊዜ የጌታ ድምፅ በቃሉ ሲናገረኝ ሰምቻለሁ፤ ስለሆነም፣ ልናወጥ አልችልም።

፮ እናም እንዲህ ሆነ እርሱ ወደ እኔ መጣና፣ በዚህ ሁኔታ እንዲህ ብሎ ተና

፳ *ሀ* ቅ.መ.መ. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ።
፳፩ *ሀ* ሞዛያ ፲፭፡ ፳፯። ቅ.መ.መ. በደል። *ለ* ቅ.መ.መ. ፍርድ፣ የመጨረሻው።
፲ *ሀ* ቅ.መ.መ. ፍትህ። *ለ* ፪ ኔፊ ፳፰፡ ፳፫። ቅ.መ.መ. ሲ.ያል። *ሐ* ት.እና ቃ. ፲፱፡ ፲–፲፪። *መ* ቅ.መ.መ. ኩነኔ።
፲፩ *ሀ* ፪ ኔፊ ፱፡ ፴፩።
፲፪ *ሀ* ሞር. ፱፡ ፳፯።
፲፫ *ሀ* አልማ ፴፣ ፲፭።
፲፮ ፩ *ሀ* ፪ ኔፊ ፲፩፡ ፫፣ ያዕቆ. ፪፡ ፲፩።

ገረኝ፥ ወንድም ያዕቆብ፣ አንተን እናገር ዘንድ ብዙ አጋጣሚዎችን ፈለግሁ፤ ወን ጌል ወይም የክርስቶስን ትምህርት ብለህ የምትጠራውን ለመስበክ እንደተጓዝክ ሰምቻለሁ እናም ደግሞ አውቄአለሁ።

፲፪ እናም ትክክለኛውን የእግዚአብ ሔር ጎዳና እንዲስቱና፣ ትክክለኛ የሆነ ውን የሙሴን ህግ ᵐእንዳይጠብቁት ከዚህ ህዝብ አብዛኛውን አስተሀል፤ እናም ከብዙ መቶ ዓመታት በኋላ ይመጣል ወደምት ለው ፍጡር አምልኮ የሙሴን ህግ ለው ጠሀል። እናም አሁን እነሆ፣ እኔ ሼረም ይህ ስድብ እንደሆነ አውጅልሀለሁ፤ ማንም ሰው የሚመጡ ነገሮችን ᵃመናገር ስለማ ይችል፣ እንደነዚህ አይነት ነገሮችን አያው ቅምና። እናም እንደዚህ ነበር ሼረም ከእኔ ጋር የተጣላው።

፲፫ ነገር ግን እነሆ፣ ጌታ እግዚአብሔር በቃሉ እስከማሳፍረው ድረስ ለነፍሴ ᵐመን ፈሱን አፈሰሰልኝ።

፲፬ እናም ለእርሱ እንዲህ አልሁ፥ የሚመ ጣውን ክርስቶስ ትክዳለህን? እና እርሱም አለ፥ክርስቶስ ከአለ አልክደውም፤ ነገር ግን ክርስቶስ እንደሌለ፣ እንዳልነበረ፣ እንደማ ይኖርም አውቃለሁ።

፲፭ እናም እንዲህ አልኩት፥ በቅዱስ መጽ ሐፍት ታምናለህ? እርሱም አዎን አለ።

፲፮ እናም እኔም አልኩት፥ አንተ እነር ሱን አትረዳቸውም፤ ምክንያቱም እነርሱ በእውነት ስለክርስቶስ ይመሰክራሉና። እነሆ፣ የትኛውም ነቢይ ክርስቶስን በተ መለከተ ከመናገር በስተቀር የፃፈ ወይም ᵐየተነበየ የለም እልሀለሁ።

፲፯ እናም ይህ ብቻም አይደለም—ይህ ለእኔ ተገልጾልኛል፣ ሰምቻለሁም ተመል ክቻለሁምና፤ እናም ይህ ደግሞ ለእኔ በመ ንፈስ ቅዱስ ᵐኃይል ተገልጾልኛል፤ ስለሆ ነም፣ ምንም አይነት የኃጢያት ክፍያ ባይ ኖር ኖሮ የሰው ዘር በሙሉ ᵃመጥፋት እን ደሚኖርበት አውቃለሁ።

፲፰ እናም እንዲህ ሆነ እርሱም አለኝ፥ አንተ በዚህ ብዙ በምታውቀው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ᵐምልክትን አሳየኝ።

፲፱ እናም አልኩት፥ ᵐእውነት መሆኑን ለምታውቀው ለአንተ ምልክት ለማሳየት እግዚአብሔርን የምፈትነው እኔ ማን ነኝ? ነገር ግን ᵃየዲያብሎስ በመሆንህ ትክደዋ ለህ። ይሁን እንጂ፣ የእኔ ፈቃድ አይሁን፤ ነገር ግን እግዚአብሔር አንተን የሚቀጣ ከሆነ ይህ በሰማይም በምድርም ኃይል እንዳለው፤ እናም ደግሞ ክርስቶስ እንደ ሚመጣ ምልክት ይሆንሃል። እናም አቤቱ ጌታ የእኔ ፈቃድ ሳይሆን ያንተ ይሆናል።

፲፳ እናም እንዲህ ሆነ እኔ ያዕቆብ እነዚ ህን ቃላት ስናገር፣ የእግዚአብሔር ኃይል ወረደበት፣ በዚህም ምክንያት መሬት ወደቀ። እናም እንዲህ ሆነ ለብዙ ቀናት እንክብካቤን አገኘ።

፲፳፩ እናም እንዲህ ሆነ ለህዝቡም ተናገረ፥ ልሞት ስለሆነ ነገ በአንድ ላይ ተሰብሰቡ፤ ስለሆነም፣ ከመሞቴ በፊት ለህዝቡ መና ገር እፈልጋለሁ።

፲፳፪ እናም እንዲህ ሆነ በማግስቱ ብዙ ዎች በአንድ ላይ ተሰበሰቡ፤ እናም ለእነ ርሱ በግልፅ ተናገረ፣ ያስተማራቸውንም ነገሮች ካደ፣ እናም ስለክርስቶስ እንዲሁም ስለመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንዲሁም ስለመ ላዕክቶች አገልግሎት መሰከረ።

፲፳፫ እናም ᵐበዲያብሎስ ኃይል ᵃተታሎ እንደነበር በግልፅ ተናገራቸው። እናም ስለ ሲ.ያልና ዘለዓለማዊነት እንዲሁም ዘለዓለ ማዊ ቅጣት ተናገረ።

፲፪ ሀ ያዕቆ. ፩፡፭።
ለ አልማ ፴፡፲፫።
፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. መነሳሻ፣ መነሳሳት።
፲፭ ሀ ራዕ. ፲፱፡፲፣ ፩ ኔፊ ፲፡፭፣ ያዕቆ. ፩፡፩፣ ሞዛያ ፲፫፡፴፫–፴፭፣ ት. እና ቃ. ፭፡፳፯።
ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ።
፲፮ ሀ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ፣ እግዚአብሔር፣ አምላክ—እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ።
ለ ፪ ኔፊ ፪፡፳፭።
፲፣ ሀ ማቴ. ፲፯፡፩–፭፣ አልማ ፴፡፴፣–፴።
ቅ.መ.መ. ምልክት።
፲፱ ሀ አልማ ፴፡፴፭–፴፱።
ለ አልማ ፴፡፴፣።
፲፳ ሀ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
ለ አልማ ፴፡፴፣።
ቅ.መ.መ. ሽንገላ (ውሸት)፣ መዋሸት፣ ማታለል።

፤፱ እናም አለ፥ ″ይቅርታ የሌለው ኃጢ
ያት በመፈፀሜ ፈርቻለሁ፣ ምክንያቱም
ለእግዚአብሔር ዋሽቻለሁና፤ ክርስቶስን
ክጃለሁና፣ ቅዱስ መጽሐፍንም አምኛለሁ
ብያለሁና፤ እነርሱም በእውነት ስለእርሱ
መስክረዋል። እናም ለእግዚአብሔር በመ
ዋሸቴ ሁኔታዬ ^መጥፎ ይሆናል ብዬ እጅግ
እፈራለሁ፤ ነገር ግን ለእግዚአብሔር እና
ዘዛለሁ።

፲ እናም እንዲህ ሆነ እነዚህን ቃላት ሲና
ገር ሌላ ምንም ማለት አልቻለም፣ እናም
″ሞተ።

፲፩ እናም ወደሞት ሲቀርብ እነዚ
ህን ነገሮች መናገሩን ህዝቡ በተመለከቱ
ጊዜ እጅግ ተደነቁ፤ እናም እንዲህም
ሆኖ ″በመሸነፍ ወደ መሬት እስከሚወ
ድቁ ድረስ የእግዚአብሔር ኃይል በእነ
ርሱ ላይ ወረደ።

፲፪ አሁን ይህ ነገር እኔን ያዕቆብን አስ
ደስቶኛል፣ ምክንያቱም በሰማይ ያለውን
አባቴን ይህን ጠይቁአለሁና፤ እርሱም
ጩኸቴን ሰምቷል፣ እናም ፀሎቴን መል
ሷል።

፲፫ እናም እንዲህ ሆነ እንደገና ሰላምና
የእግዚአብሔር ፍቅር በህዝቡ መካከል
ዳግሞ ተመለሰ፤ እናም ቅዱሳን መጻሕፍ
ትን ″መረመሩና፣ የዚህን የኃጢአተኛውን
ሰው ቃል ከእንግዲህ አላዳመጡም።

፲፬ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያንን ወደ
እውነተኛ እውቀት ″ለመመለስ ብዙ ዘዴ
ዎች ተቀይሰው ነበር፤ ነገር ግን ^በጦርነትና
ሐደም መፋሰስ ስለሚደሰቱና፣ ከእኛ ከወን
ድሞቻቸው ዘለዓለማዊ የሆነ ՞ጥላቻ ስለነበ
ራቸው ሁሉም ″በከንቱ ነበሩ። እናም በጦር
መሳሪያዎቻቸው ኃይል ሁልጊዜም ሊያጠ
ፉን ፈለጉ።

፲፭ ስለሆነም፣ የኔፊ ህዝብ በእነርሱ ላይ
ከነመሳሪያዎቻቸው፣ እናም በሙሉ ኃይላ
ቸው፣ የደህንነታቸው ″አለት በሆነው በእ
ግዚአብሔር በማመን መሸጉ፤ ስለሆነም
ጠላቶቻቸውን በማሸነፍ ቀጠሉ።

፲፮ እናም እንዲህ ሆነ እኔ ያዕቆብ
መሸምገል ጀመርኩ፤ እናም የዚህ ህዝብ
ታሪክ ″በሌላኛው የኔፊ ሰሌዳዎች በመቀ
መጡ፣ ስለሆነም፣ ባለኝ እውቀት መፃፌን
በመናገር፣ ጊዜው ከእኛ ጋር አልፏል፣
እናም ደግሞ ^ህይወታችን ልክ እንደ
ህልም አልፏል፤ ከኢየሩሳሌም ተጥለን
ወጥተን ስደተኞች በመሆናችን፣ በምድ
ረበዳ ውስጥ በመከራ ስለተወለድን፣ እናም
በራሳችን ወንድሞች ስለተጠላን፣ ይህም
ጦርነትና ፀብን ስላስነሳ፣ ብቸኛና ጭምት
ሰዎች ነበርን በማለትይህንን ታሪክ አጠ
ቃልላለሁ፤ ስለሆነም፣ በዘመናችን ሁሉ
አለቀስን።

፲፯ እናም እኔ ያዕቆብ፣ በቅርቡ ወደ
መቃብሬ መሄድ እንዳለብኝ ተመለከትኩ፣
ስለሆነም፣ ለልጄ ″ኢኖስ አልኩት፥ እነዚ
ህን ሰሌዳዎች ውሰድ። እናም ወንድሜ ኔፊ
^ያዘዘኝን ነገሮች ነገርኩትና እርሱም ለትዕ
ዛዛቱ ታዛዥ ለመሆኑ ቃል ገባ። እናም በእ
ነዚህ ሰሌዳዎች ላይ ጥቃቅን የሆኑትን ጽሁ
ፎችን መፃፌን ጨረስኩ፤ አብዛኞቹ ወን
ድሞቼ ቃሌን እንደሚያነቡ በማመን ለአ
ንባቢያን ደህና ሁኑ እላለሁ። ወንድሞች
ደህና ሁኑ።

፤፱ ሀ ቅ.መ.መ. ይቅርታ የሌለው
ኃጢያት።
ለ ሞዛያ ፤፭፡ ፳፤።
፳ ሀ ኤር. ፳፰፡ ፤፭–፤፯።
፳፩ ሀ አልማ ፤፱፡ ፤።
፳፫ ሀ አልማ ፤፯፡ ፪።
፳፬ ሀ ኢኖስ ፩፡ ፳።

ለ ሞዛያ ፤፡ ፤፩–፤፳፤።
ሐ ጄረም ፩፡ ፣፤
አልማ ፳፤፡ ፳፫–፳፭።
መ ፪ ኔፊ ፭፡ ፩–፫፣
ሞዛያ ፳፰፡ ፪።
ሠ ኢኖስ ፩፡ ፤፬።
፳፭ ሀ ቅ.መ.መ. አለት።

፳፤ ሀ ፩ ኔፊ ፤፱፡ ፩–፣
ጄረም ፩፡ ፤፬–፤፭።
ቅ.መ.መ. ሰሌዳዎች።
ለ ያዕ. ፬፡ ፤፬።
፳፯ ሀ ኢኖስ ፩፡ ፩።
ለ ያዕቆ. ፩፡ ፩–፬።

መፅሐፈ ኢኖስ

ኢኖስ በኃይል ፀለየ እናም ለኃጢአቱ ስር የትን አገኘ—ለላማናውያን ወደፊት በሚ መጣው ደህንነታቸው ተስፋ ያለው የጌታ ድምፅ ወደ አዕምሮው መጣ—ኔፋውያን ላማናውያንን ለመመለስ ጣሩ—ኢኖስ በቤዛው ይደሰታል። ከ፴፪፹ ም.ዓ. ገደማ።

እነሆ፣ እንዲህ ሆነ እኔ ᵐኢኖስ ᵃአባቴ ፃድቅ ሰው እንደነበር ስለማውቅ—በራሱም ቋንቋ እናም ደግሞ በጌታ ᵃᵇአስ ተዳደግና ተግሳፅ ᶜᵈስላስተማረኝ፣ እናም ለዚህ የአምላኬ ስም የተባረከ ይሁን—

፪ እናም ᵉᶠለኃጢአቴ ስርየትን ከማግ ኘቴ በፊት በእግዚአብሔር ፊት ስለነበረኝ ᵃትግል እነግራችኋለሁ።

፫ እነሆ፣ አራዊትን ለማደን ወደጫካው ሄድኩ፤ እናም አባቴ ዘለዓለማዊ ህይወት ንና የቅዱሳንን ᵍደስታ በተመለከተ ሁል ጊዜ ሲናገር የምሰማቸው ቃላት ወደልቤ ᵃጠልቀው ገቡ።

፬ እናም ነፍሴ ᵉተራበች፤ በፈጣሪዬም ፊት ᵃተንበረከክሁ፣ እናም ለነፍሴ በሀይ ለኛ ᵇᶜፀሎትና ልመና ወደእርሱ ጮህኩኝ፣ እናም ቀኑን ሙሉ ወደ እርሱ ጮህኩኝ፤ አዎን፣ ምሽቱ ሲመጣ ድምፄን ሰማይ እስ ከሚደርስ ከፍ አደረግሁት።

፭ እናም ᵉድምፅ ወደእኔ መጣ፣ እንዲህም አለኝ፥ ኢኖስ ኃጢያትህ ይቅር ተብሎል ሃል እናም አንተ ትባረካለህ።

፮ እናም እኔ ኢኖስ እግዚአብሔር ሊዋሽ እንደማይችል አውቃለሁ፤ ስለሆነም፣ በደሌ ተወግዶልኛል።

፯ እናም ጌታ፣ ይህ እንዴት ሆነ? አልኩት።

፰ እናም እርሱም አለኝ፥ ባላየኸውና ሰምተህ በማታውቀው በክርስቶስ ባለህ ᵉእምነት ምክንያት ነው። እናም እራ ሱን በአካል ከመግለፁ በፊት ብዙ አመ ታት ያልፋሉ፤ ስለሆነም፣ ሂድ እምነትህ ᵃአድኖሃል።

፱ አሁን፣ እንዲህ ሆነ እነዚህን ቃላት በም ሰማ ጊዜ ለኔፋውያን ወንድሞቼ ደህንነት ᵉማሰብ ጀመርኩ፤ ስለሆነም፣ ለእነርሱ ነፍ ሴን ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ᵃአፈሰስኩ።

፲ እናም እንደዚህ በመንፈስ በምታገል በት ጊዜ፣ እነሆ፣ የጌታ ድምፅ ᵉበአዕም ሮዬ በድጋሚ መጥቶ እንዲህ አለኝ፤ ወን ድሞችህ ትዕዛዛቴን ለመጠበቅ ባላቸው ትጋት መሰረት እጎበኛቸዋለሁ። ለእነር ሱም ይህን ምድር ᵃሰጥቻቸዋለሁ፣ ይህ ችም ቅዱስ ምድር ናት፤ በክፋት የተነሳ ካልሆነ በቀር ᵇᶜአልረግማትም፤ ስለሆነም፣ በተናገርኩት መሰረት ወንድሞችህን እጎበ ኛቸዋለሁ፤ እናም መተላለፋቸውን በራሳ ቸው ላይ በሀዘን አወርዳለሁ።

፲፩ እናም እኔ ኢኖስ፣ እነዚህን ቃላት ከሰማሁ በኋላ እምነቴ በጌታ የማይናወጥ ሆነ፤ እናም ለወንድሞቼ ላማናውያን በብዙ ረጅም ትግል ወደ እርሱ ፀለይኩ።

፲፪ እናም እንዲህ ሆነ ባለኝ በሙሉ ትጋት

፩ ፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. ኢኖስ፣ የያዕቆብ ልጅ።
ለ ፪ ኔፊ ፪፡፪–፬።
ሐ ኤፌ. ፮፡፬።
መ ፩ ኔፊ ፩፡፩–፪።
፪ *ሀ* ቅ.መ.መ. የኃጢያት ስርየት።
ለ ዘፍጥ. ፴፪፡፳፭–፴፪፤ አልማ ፳፡፲።
ቅ.መ.መ. መጸጸት፣ ንስሀ መግባት።
፫ *ሀ* ቅ.መ.መ. ደስታ።
ለ ፩ ኔፊ ፲፡፲፯–፲፱፤ አልማ ፴፯፡፲፯–፳፩።
፬ *ሀ* ፪ ኔፊ ፱፡፶፣ ፫ ኔፊ ፲፫፡፲፤ አልማ ፴፯፡፲፣ ፳፩–፳፪።
ለ ቅ.መ.መ. ማክበር።
ሐ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
፭ *ሀ* ቅ.መ.መ. ራዕይ።
፮ *ሀ* ኤተር ፫፡፲፪–፲፫።
ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
ለ ማቴ. ፱፡፳፪።
፱ *ሀ* ፩ ኔፊ ፰፡፲፤ ፲፪፤ አልማ ፴፡፲፣ ፳–፳፪።
ለ ፪ ኔፊ ፡ ፡ ፣ ቃላት ፩፡፰፤ አልማ ፴፡፲–፳፯–፳፯።
፲ *ሀ* ቅ.መ.መ. መነሳሻ፣ መነሳሳት፤ አዕምሮ።
ለ ፩ ኔፊ ፪፡፳።
ሐ ኤተር ፪፡፲–፲፪።

ከሰራሁና [ሀ]ከፀለይኩ በኋላ፣ ጌታም አለኝ፥ በእምነትህ የተነሳ [ለ]እንደተመኘኸው መሰረት እሰጥሀለሁ።

፲፫ እናም አሁን እነሆ፣ ከእርሱ የፈለግሁት ፍላጎት ይህ ነበር—የእኔ ህዝብ ኔፋውያን በመተላለፋቸው መውደቅ ካለባቸውና በምንም አይነት [ሀ]መጥፋትም ቢኖርባቸው፣ ላማናውያንም መጥፋት ከሌለባቸው፣ ጌታ አምላክ የህዝቤን የኔፋውያን ታሪክ [ለ]እንዲጠብቅ ዘንድ፤ እንዲሁም፣ በቅዱስ ክንዱ ኃይልም እንኳን ቢሆን፣ ይህም ወደፊት አንድ ቀን ለላማናውያን [ሐ]ይመጡ ዘንድ፣ ምናልባት ወደ ደህንነት [መ]ይመጡ ዘንድ—

፲፬ ለጊዜው እነርሱን ወደ እውነተኛው እምነት የመመለሱ ትግል [ሀ]ከንቱ ነበር። እናም ታሪካችንና እኛን፣ ደግሞም የአባቶቻችንን ባህል ሁሉ የሚቻላቸው ከሆነ [ለ]ያጠፉ ዘንድ በቁጣቸው ማሉ።

፲፭ ስለሆነም፣ ጌታ እግዚአብሔር ታሪካችንን [ሀ]ማስቀመጥ እንደሚቻለው ስለማውቅ፣ ያለማቋረጥ ወደ እርሱ ጮህኩኝ፣ እርሱም እንዲህ ብሎኛልና፥ በክርስቶስ ስም እንደምትቀበል ካመንህ ምንም ነገር በእምነት ብትጠይቅ ትቀበላለህ።

፲፮ እናም እኔ እምነት ነበረኝ፣ እናም [ሀ]መዝገቦቹን [ለ]እንዲያስቀምጥ ወደ እግዚአብሔር ጮህኩ፤ በእርሱ ዘመን ለላማናውያን [ሐ]እንደሚያመጣውም ከእኔ ጋር ቃል ኪዳን ገባ።

፲፯ እናም እኔ ኢኖስ፣ በገባው ቃል ኪዳን መሰረት እንደሚሆን አውቃለሁ፤ ስለዚህ ነፍሴም እረፍትን አገኘች።

፲፰ እናም ጌታ አለኝ፥ አባቶችህም ደግሞ ስለዚህ ነገር ከእኔ ይፈልጉ ነበር፤ እናም ለእነርሱ እንደእምነታቸው ይደረግላቸዋል፤ እምነታቸው ልክ እንደአንተው ነበርና።

፲፱ እናም አሁን እንዲህ ሆነ እኔ ኢኖስ፣ የሚመጡትን ነገሮች በመተንበይ በኔፋውያን ህዝብ መካከል ተጓዝኩ፣ እናም የሰማኋቸውንና ያየኋቸውን ነገሮች መሰከርኩ።

፳ እናም የኔፊ ህዝብ ላማናውያንን ወደ እውነተኛው የእግዚአብሔር እምነት እንዲመልሱ በትጋት እንደሚመክሩ እመሰክራለሁ። ነገር ግን [ሀ]ስራችን ከንቱ ነበር፤ ጥላቻቸው የፀና ነበር፣ እናም በመጥፎ ተፈጥሮአቸው ተመርተው ስለነበር አረመኔ፣ አስፈሪም፣ [ለ]ደም የተጠማ ህዝብና፣ [ሐ]ጣኦትን አምላኪና ርኩሳን ሆኑ፤ የታደኑ አውሬዎችን በመመገብ፤ በድንኳን መኖርና፣ በምድረበዳ ውስጥ አጭር የቆዳ ግልድም አገልድመው እራሳቸውን ተላጭተው ተዘዋወሩ፤ እናም ችሎታቸውም [መ]ስለቀስትና ደጋን እንዲሁም ምሳር ነበር። እናም ብዙዎች ከጥሬ ስጋ በስተቀር ምንም አይበሉም ነበር፤ እናም እነሱ ያለማቋረጥ እኛን ለማጥፋት ይፈለጉ ነበር።

፳፩ እናም እንዲህ ሆነ የኔፊ ህዝብ መሬትን ያርሱ ነበር፣ እናም ሁሉንም አይነት እህልና ፍራፍሬ [ሀ]ያበቅሉ፣ የከብት መንጋዎችን፣ ከሁሉም የከብት አይነት መንጋዎችን፣ ፍየሎችን፣ የሜዳ ፍየሎችን፣ እናም ደግሞ ብዙ ፈረሶችን ያረቡ ነበር።

፳፪ እናም ከእኛ መካከል እጅግ ብዙ [ሀ]ነቢያት ነበሩ። እናም ህዝቡ ለመረዳት የሚያስቸግር [ለ]አንገተ ደንዳና ነበር።

፳፫ እናም እጅግ [ሀ]አስከፊ ከሆነው የጦርነት

፲፪ ሀ ሞር. ፰፥ ፳፭፤ ፱፥ ፴፮።
ለ መዝ. ፴፯፥ ፬፤
፩ ኔፊ ፯፥ ፲፪፤ ሔለ. ፲፥ ፭።
፲፫ ሀ ሞር. ፮፥ ፩፤ ፮።
ለ ቃላት ፩፥ ፮–፲፩፤
አልማ ፴፯፥ ፪።
ሐ አልማ ፴፯፥ ፲፱፤
ኤተር ፲፪፥ ፳፪፤
ት. እና ቃ. ፫፥ ፲፰።
መ አልማ ፱፥ ፲፯።
፲፬ ሀ ያዕቆ. ፯፥ ፳፬።
ለ ሞር. ፮፥ ፮።
፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. ቅዱሳት መጻህፍት—የሚጠበቁ ቅዱስ መጻፍህት።
፲፮ ሀ ቅ.መ.መ. መፅሐፈ ሞርሞን።
ለ ፫ ኔፊ ፭፥ ፲፫–፲፭፤
ት. እና ቃ. ፫፥ ፲፱–፳፤
፲፥ ፵፮–፶።
ሐ ፪ ኔፊ ፳፯፥ ፮።
፳ ሀ ሞሮኒ ፱፥ ፮።
ለ ጄረም ፩፥ ፮።
ሐ ሞዛያ ፱፥ ፲፪።
ቅ.መ.መ. ጣኦት አምላኪ።
መ ሞዛያ ፲፥ ፰።
፳፩ ሀ ሞዛያ ፱፥ ፱።
፳፪ ሀ ቃላት ፩፥ ፲፮–፲፰።
ለ ጄረም ፩፥ ፫።
፳፫ ሀ ፩ ኔፊ ፲፮፥ ፪፤
፪ ኔፊ ፴፫፥ ፭።

ᵃሰበካና ትንቢት፣ እናም ፀብና ጥፋት፣ እን ዲሁም ያለማቋረጥ ሞትን ᵇከሚያስታውሳ ቸውና፣ ከዘለዓለማዊ ጊዜ፣ ፍርድና ከእግ ዚአብሔር ኃይል፣ በጌታ ፍርሃት ᶜያለማ ቋረጥም ይጠበቁ ዘንድ ካነሳሳቸው በስተቀር ምንም የለም። ከእነዚህ ነገሮችና እጅግ ታላቅ የሆነው ግልፅ ንግግር በስተቀር ወደ ጥፋት በፍጥነት ከመሄድ የሚጠብቃቸው ምንም ነገር አልነበረም እላለሁ። እናም በእንደዚህ አይነት እነሱን በተመለከተ እፅፋለሁ።

፳፬ እናም በጊዜዬ በኔፋውያንና በላማና ውያን መካከል ጦርነቶችን ተመልክቻለሁ።

፳፭ እናም እንዲህ ሆነ እየሸመገልኩ ሄድኩ፣ እናም አባታችን ሌሂ ኢየሩሳሌ ምን ᵈለቆ ከወጣ አንድ መቶ ሰባ ዘጠኝ አመ ታት አለፉ።

፳፮ እናም በእግዚአብሔር ኃይል ለዚህ ህዝብ መስበክና እንድተነብይ፣ እናም በክ ርስቶስ ባለው እውነት መሰረት ቃሉን እን ድናገር እንደተገፋፋሁ በቶሎ ወደ መቃ ብሬ መሄድ እንዳለብኝ ተመለከትኩ። እናም በዘመኔ ሁሉ ተናግሬዋለሁ፣ በዚ ህም ከዓለም በላይ ተደስቼበታለሁ።

፳፯ እናም ከቤዛዬ ጋር ወደሆነው ᵉማረ ፊያዬ በቶሎ እሄዳለሁ፤ በእርሱ እንደማርፍ አውቃለሁና። እናም ᶠየሚሞተው ሟየይ ሞተውን በሚተካበትና፣ በእርሱ ፊት በም ቆምበት ቀን እደሰታለሁ፤ ከእዚያም ፊቱ ንም በደስታ አያለሁ፣ እርሱም ይለኛል፥ የተባረከው ወደ እኔ ና፣ በአባቴም ᵐቤት የተዘጋጀልህ ቦታ አለ። አሜን።

መፅሐፈ ጄረም

ኔፋውያን የሙሴን ህግ ጠበቁ፣ የክርስ ቶስንም መምጣት ጠበቁ፣ እናም በምድ ሪቱ ላይ በለፀጉ—ብዙ ነቢያት ሕዝቡን በእውነት ጎዳና ለመጠበቅ ጣሩ። ከ፫፻፶፯–፫፻፷፩ ም.ዓ. ገደማ።

ᵃሁን እነሆ፣ እኔ ጄረም፣ በአባቴ፣ ኢሮስ ትዕዛዝ መሰረት የእኛ ᵇየትው ልድ ሐረግ ይጠበቅ ዘንድ ጥቂት ቃላት እፅ ፋለሁ።

፪ እናም ᶜእነዚህ ሰሌዳዎች ᵃትንሽ ቦታ ያላቸው በመሆኑ፣ እና እነዚህ ነገሮች ᵈየሚፃፉት ለወንድሞቻችን ᵉላማናውያን ጥቅም ስለሆነ፣ በመሆኑም ጥቂት መፃፌ አስፈላጊ ነው፤ ነገር ግን የእኔን ትንቢትም ሆነ ራዕይ አልፅፍም። አባቶቼ ከጻፉትስ የበ ለጠ ምን መፃፍ ይቻለኛል? እነርሱ የደህ ንነትን ዕቅድ አልገለጹምን? እኔ እላችኋ ለሁ፣ አዎን፣ እናም ይህ ለእኔ ብቁ ነው።

፫ እነሆ፣ በልባቸው ጠጣርነትና፣ በጆሮ አቸው መደንቆር፣ እናም በአዕምሮአቸው መታወርና፣ ᶠበአንገተ ደንዳናነታቸው ምክንያት፤ በዚህ ህዝብ መካከል ብዙ መስ ራቱ አስፈላጊ ነው፤ ይሁን እንጂ፣ እግዚአ ብሔር ለእነርሱ እጅግ መሀሪ ነው፣ እናም እስከአሁንም ከምድረ ገፅ ᵃአላጠፋቸውም።

፳፫ ᵃ ቅ.መ.መ. መስበክ።
ᵇ ሐሌ. ፲፪፡፫።
ᶜ ጄረም ፩፡፲፪፤ አልማ ፴፩፡፭።
፳፭ ᵃ ፩ ኔፊ ፪፡፪–፴።
፳፯ ᵃ ቅ.መ.መ. እረፍት።
ᵇ ቅ.መ.መ. ስጋዊ፣ የሚሞት።
ᶜ ቅ.መ.መ. የማይሞት፣ አለሟችነት።
ᵈ ዮሐ. ፲፬፡፪–፫፤ ኤተር ፲፪፡፴፪–፴፴፤ ት. እና ቃ. ፷፪፡፭፤ ፶፰፡፲፰።

[ጄረም]
ᵃ ፩ ᵇ ፩ ኔፊ ፫፡፲፪፤ ፭፡፲፬።
ᶜ ᵃ ያዕቆ. ፫፡፲፬፤ ኦምኒ ፩፡፩።
ᵈ ፩ ኔፊ ፯።
ᵉ ሐ ቅ.መ.መ. ቅዱሳት መጻህፍት—የቅዱሳት መጻህፍት ዋጋዎች።
ᶠ ᵃ ፩ ኔፊ ፳፯፡፯፤ ሞር. ፭፡፲፪።
፫ ᵃ ኢሮስ ፩፡፳፪–፳፫።
ᵇ ኤተር ፪፡፳–፲።

፬ እናም ብዙ ᵐራዕይ ያላቸው ብዙዎች በመካከላችን አሉ፤ ምክንያቱም ሁሉም አንገተ ደንዳና አይደሉምና። እናም አን ገተ ደንዳና ያልሆኑና እምነት ያላቸው ሁሉ፤ እንደ እምነታቸው፣ ለሰው ልጆች ነገሮችን ከሚገልፀው ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ᵃህብረት አላቸው።

፭ እናም አሁን፣ እነሆ፣ ሁለት መቶ ዓመ ታት አለፉ፣ የኔፊ ህዝቦች በምድሪቷ ላይ በረቱም። የሙሴን ህግና ᵐየሰንበትን ቀን ለጌታ ቅዱስ አድርገው ᵃበመጠበቅ አስተ ዋሉ። ᶜይማኖትንም ᵈአላረከሱም፤ ወይም ᵉአይሳደቡም። እናም የምድሪቷን ህጎች እጅግ የጠበቁ ነበሩ።

፮ እናም እነርሱና፣ ላማናውያን ደግሞ በምድሪቱ ገፅ ላይ በብዛት ተበታትነው ነበር። እናም ከኔፋውያን ይበልጥ እጅግ ብዙ ነበሩ፤ እናም ᵐመግደል ይወዱ ነበ ርና፣ የዓራዊትን ደም ይጠጡ ነበር።

፯ እናም እንዲህ ሆነ፣ ከእኛ ከኔፋውያን ጋር ለመዋጋት ብዙ ጊዜ መጥተው ነበር። ነገር ግን ᵐነገሥታቶቻችንና መሪዎቻችን በጌታ እምነት ᶜያል ሰዎች ነበሩ፤ እናም ህዝቡን የጌታን መንገድ አስተማሩ፤ ስለሆ ነም፣ እኛ ላማናውያንን ተቋቋምን፣ እንዲ ሁም ᵃከምድራችን አስወገድናቸው፣ እናም ለከተሞቻችን ወይም የውርሳችን ቦታ የሆነ ውን ማንኛውንም መከላከያ መስራት ጀመ ርን።

፰ እናም እጅግ ተባዛንና፣ በምድሪቱ ገፅ ላይ ተሠራጨን፣ እናም በወርቅና በብር እንዲሁም በከበሩ ነገሮችና፣ በመልካም የእንጨት ጥበብም፣ በመገንባትም፣ በማ ሽኖችም፣ እንዲሁም ደግሞ በብረትና መዳብ፣ እንዲሁም በነሀስ ምድሩን ለማ ረስ የሚያስችሉ መሳሪያዎችን እንዲሁም ᵐየጦር መሳሪያዎች በመስራት፣ አዎን ሹል ጫፍ ያለው ቀስትና፣ ሰይፍ፣ ጦር እናም ለጦርነት ሁሉንም አይነት ዝግጅት በማ ድረግ እጅግ ሀብታም ሆንን።

፱ እናም ላማናውያንን ለመገናኘት እንደ ዚህ እየተዘጋጀን እያለን፣ እነርሱ በእኛ ላይ ሊያይሉብን አልቻሉም። ነገር ግን ለአባ ቶቻችን እንዲህ በማለት የተናገረው የጌታ ቃል ተረጋግጦ ነበር፥ እናንተ የእኔን ትዕዛ ዛት እስከጠበቃችሁ ድረስ በምድሪቱ ላይ ትበለፅጋላችሁ።

፲ እናም እንዲህ ሆነ የጌታ ነቢያት በእ ግዚአብሔር ቃል መሰረት እነርሱ ትዕዛ ዛትን ካልጠበቁ፣ ነገር ግን ወደ መተላለፍ ከወደቁ፣ ከምድር ፊት ᵐመጥፋት እንዳለ ባቸው የኔፊን ህዝብ አስፈራርተው ነበር።

፲፩ ስለሆነም በነቢያትና፣ ካህናትና፣ መምህራን ህዝቦችን የሙሴን ᵐህግጋትና የተሰጠበትን አላማ በማስተማር፣ ወደመ ሲህ ወደፊት ᵃእንዲመለከቱና እርሱ ᵇእን ደመጣም አይነት እንደሚመጣ እንዲያምኑ በትእግስት አጥብቀው በመምከር በትጋት አገለገሉ። እናም በዚህ ሁኔታ አስተምረ ዋቸው ነበር።

፲፪ እናም እንዲህ ሆነ ይህን በማድረግ ከምድር ፊት ᵐእንዳይጠፉ ጠበቋቸው፤ ልባቸውንም በቃላት ᵃወቀሱት፣ በማከታ ተልም ለንስሀ አነሳሷቸው።

፲፫ እናም እንዲህ ሆነ ለብዙ ጊዜ ከነበረው የጦርነትና ግጭት እንዲሁም የፀብ ሁኔታ ሁለት መቶ ሠላሳ ስምንት ዓመታት አለፉ።

፲፬ እናም እኔ ጆረም፣ ሰሌዳዎቹ ትንሽ በመሆናቸው፣ ከዚህ የበለጠ አልፅፍም። ነገር ግን እነሆ፣ ወንድሞቼ፣ ወደ ᵐሌላኛው

፬ ሀ አልማ ፳፯፡፳፪፣
ሔሊ. ፲፭፡፳፫፣
ት. እና ቃ. ፍ፯፡፲፳–፲፱።
ቅ.መ.መ. ራዕይ።
ለ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
፭ ሀ ዘፀአ. ፴፭፡፪።
ቅ.መ.መ. የሰንበት ቀን።
ለ ፪ ኔፊ ፳፭፡፳፬፣
አልማ ፴፡፡ ፲፫–፲፡።
ሐ ቅ.መ.መ. ማራከስ።
መ ቅ.መ.መ. መስደብ።
፮ ሀ ያዕቆ. ፣፡፳፣
ኢኖስ ፭፡፳።
፯ ሀ ያዕቆ. ፭፡፱፣ ፲፭፣ ፲፭።
ለ ቃላት ፭፡፲፡።
፰ ሀ ሞዛያ ፲፡፰።
፲ ሀ ፩ ኔፊ ፲፪፡፲፱–፳፣
ኦምኒ ፭፡፭።
፲፩ ሀ ያዕቆ. ፡፡ ፣
አልማ ፳፭፡፲፭–፲፮።
ለ ፪ ኔፊ ፲፭፡፡፣
ኤተር ፲፪፡፲፰–፲፱።
ሐ ፪ ኔፊ ፳፭፡፳፡–፳፮፣
ሞዛያ ፫፡፲፫፣ ፲፮፡፮።
፲፪ ሀ ኤተር ፪፡፲።
ለ አልማ ፴፭፡፭።
፲፡ ሀ ፩ ኔፊ ፱፡፪–፡።

የኔፊ ሰሌዳዎች መሄድ ትችላላችሁ፤ እነሆ፣ በእነርሱ ላይ ይፃፉ ዘንድ ባደረጉት፣ ወይም እንደ ነገሥታቱ አፃፃፍ የጦርነት ታሪኮች ተቀርፀዋል።

፲፰ እናም እንደ አባቶቼ [ሀ]ትዕዛዛት መሰረት ይጠበቁ ዘንድ እነዚህን ሰሌዳዎች ለወንድ ልጄ፣ ለኦምኒ፣ አስረክባለሁ።

መፅሐፈ ኦምኒ

ኦምኒ፣ አማሮን፣ ቼሚሽ፣ አቢናዶም፣ እና፣ አማሌቂ እያንዳንዳቸው በተራ መዝገቡን አስቀመጡ—ሞዛያ በሴዴቅያስ ዘመን ከኢየሩሳሌም የመጡትን፣ የዛራሔምላን ህዝብ አገኘ—ሞዛያ በእነርሱ ላይ እንዲነግስ ተደረገ—በዛራሔምላ የሙሌቅ ዘርያዎች የያሬዳውያን መጨረሻ የሆኑትን፣ ቆሪያንተመርን አገኙ—ንጉስ ቢንያም ሞዛያን ተካ—ሰዎች ለክርስቶስ እንደሚቀርብ መስዋዕት ነፍሳቸውን መስዋዕት ማድረግ ይኖርባቸዋል። ከ፫፻፳፫–፩፻፴ ም.ዓ. ገደማ።

እነሆ እንዲህ ሆነ እኔ ኦምኒ፣ በአባቴ ጄረም በመታዘዜ፣ የትውልዳችንን ሐረግ ለማቆየት በእነዚህ ሰሌዳዎች ላይ ጥቂት መፃፍ አለብኝ—

፪ ስለሆነም፣ በዘመኔ ህዝቤን ኔፋውያንን በጠላቶቻቸው ላማናውያን እጅ እንዳይወድቁ ለመጠበቅ በሰይፍ ብዙ መዋጋቴን እንድታውቁልኝ እፈልጋለሁ። ነገር ግን እነሆ፣ እኔ ራሴ ኃጢአተኛ ሰው ነኝ፣ እናም ማድረግ እንደሚገባኝ የጌታን ህግና ትዕዛዛት አልጠበቅሁም።

፫ እናም እንዲህ ሆነ ሁለት መቶ ሰባ ስድስት አመታት አለፉ፣ ብዙ የሰላም ወቅት ነበረንም፤ እናም ብዙ የከፋ ጦርነትና የደም መፋሰስ ወቅት ነበረን። አዎን፣ በአጠቃላይ ሁለት መቶ ሰማንያ ሁለት ዓመታት አለፉ፣ እናም እነዚህን ሰሌዳዎች እንደ አባቶቼ [ሀ]ትዕዛዝ አስቀመጥሁት፤ እነርሱንም ለልጄ አማሮን ሰጠሁ። እናም አበቃሁ።

፬ እናም አሁን እኔ አማሮን፣ ጥቂት የሆኑትን በአባቴ መፅሐፍ ውስጥ የፃፍኩትን ፅፌአለሁ።

፭ እነሆ፣ እንዲህ ሆነ ሶስት መቶ ሀያ ዓመታት አለፉ፣ እናም እጅግ ክፉ የሆኑት ኔፋውያን [ሀ]ጠፉ።

፮ ምክንያቱም ጌታ እነርሱን ከኢየሩሳሌም ምድር ካስወጣቸውና በጠላቶቻቸው እጅ እንዳይወድቁ ባለመፍቀዱ ጠብቆ ካቆያቸው በኋላ፣ አዎን፣ ለአባቶቻችን እናንተ ትዕዛዛቴን እስካልጠበቃችሁ ድረስ በምድሪቱ ላይ አትበለፅጉም ብሎ የተናገረው ቃል እንዳይረጋገጥ አይፈቅድምና።

፯ ስለሆነም፣ ጌታ በታላቅ ፍርድ ጎብኝቷቸዋል፤ ይሁን እንጂ፣ ፃድቃኖችን እንዳይጠፉ አስቀርቷል፣ ነገር ግን እነርሱን ከጠላቶቻቸው እጅ አድኗቸዋል።

፰ እናም እንዲህ ሆነ ሰሌዳዎቹን ለወንድሜ ቼሚሽ ሰጠሁት።

፱ እናም እኔ ቼሚሽ ወንድሜ በፃፈበት መፅሐፍ ላይ የምፅፋቸውን ጥቂት ነገሮችን ፃፍኩ፤ እነሆም በመጨረሻ በራሱ እጅ የፃፋቸውን ተመልክቻለሁ፤ ይህንንም የጻፈው እርሱ ለእኔ በሰጠኝ ቀን ነበር። እናም እንደ አባቶቻችን ትዕዛዛት መሰረት መዝ

፲፰ ሀ ያዕቆ. ፩፥፩–፬።

[ኦምኒ]
፩ ፫ ሀ ያዕቆ. ፩፥፩–፬፤ ጄረም ፩፥፲፰።
፭ ሀ ጄረም ፩፥፱–፲።

ገቡን ጠብቀን ያቆየናቸው በዚህ መልኩ ነበር። እናም አበቃለሁ።

፲ እነሆ፣ እኔ አቢናዶም፣ የቼሚሽ ልጅ ነኝ። እነሆ እንዲህ ሆነ በህዝቤ በኔፋውያንና በላማናውያን መካከል ብዙ ጦርነቶችንና ፀቦችን ተመልክቻለሁ፤ እናም እኔ ወንድሞቼን ለመከላከል በራሴ ሰይፍ የብዙ ላማናውያንን ነፍስ አጥፍቻለሁ።

፲፩ እናም እነሆ፣ የዚህ ህዝብ ታሪክ የተቀረፀው ነገሥታቱ በነበሩአቸው ሰሌዳዎች ላይ እንደ ትውልዳቸው መሰረት ነው፤ እና እኔ ከተፃፉት በስተቀር ትንቢትም ሆነ ራዕይ አላውቅም፤ ስለሆነም፣ የተፃፉት በቂ ናቸው። እናም አበቃለሁ።

፲፪ እነሆ፣ እኔ አማሌቂ፣ የአቢናዶም ልጅ ነኝ። እነሆ፣ የዛራሔምላ ምድር ንጉስ ስለሆነው ሞዛያ ጥቂት እናገራለሁ፤ እነሆም ᐸከኔፊ ምድር እንዲወጣ፣ እናም የጌታን ድምፅ የሰሙ ደግሞ ብዙዎችም ከእነርሱ ጋር ወደ ምድረበዳው ᐹመሸሽ እንዳለባቸው በጌታ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ስለነበረ—

፲፫ እናም እንዲህ ሆነ ጌታ እንዳዘዘው አደረገ። እናም ብዙዎች የጌታን ድምፅ የሰሙ ወደ ምድረበዳው ሸሹ፤ በብዙ ስብከትና ትንቢቶችም ይመሩ ነበር። እናም ያለማቋረጥ በእግዚአብሔር ቃል ተገሰፁ፤ በምድረበዳ ውስጥ ዛራሔምላ ወደሚባለው ምድር እስከሚመጡ ድረስ በክንዱ ኃይልም ተመሩ።

፲፬ እናም የዛራሔምላ ህዝብ ተብለው የሚጠሩትን ህዝቦች አገኙ። ᐸበዛራሔምላ ህዝብ መካከል አሁን ታላቅ ደስታ ነበር፤ እናም ደግሞ ዛራሔምላ እጅግ ተደሰተ፣ ምክንያቱም ጌታ የአይሁዶችን ታሪክ ከያዘው ᐹየነሀስ ሰሌዳዎች ጋር የሞዛያን ህዝብ ልኳልና።

፲፭ እነሆ፣ እንዲህ ሆነ ሞዛያ፣ የይሁዳ ንጉስ ᐸሴደቅያስ፣ ወደ ባቢሎን በምርኮ በተወሰደበት ጊዜ ᐹየዛራሔምላ ህዝብ ከኢየሩሳሌም እንደወጡ ተረዳ።

፲፮ እናም በምድረበዳ ውስጥ ተጓዙ፤ እናም በጌታ እጅ ሞዛያ ወዳገኘው ምድር ታላቁን ውሃ ተሻገሩ፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በዚያ ኖሩም።

፲፯ እናም ሞዛያ ባገኛቸው ጊዜ፣ በቁጥር እጅግ ብዙ ነበሩ። ይሁን እንጂ፣ ብዙ ጦርነትና የከፋ ፀብ ነበራቸው፣ እናም ከጊዜ ወደ ጊዜ በሰይፍ ወደቁ፤ ቋንቋቸውም ተበላሽቶ ነበር፣ ምንም የታሪካቸውንም ᐸመዝገብ አላመጡም ነበር፤ እንዲሁም ፈጣሪያቸው መኖሩን ካዱ፣ እናም ሞዛያ ወይም የሞዛያ ህዝብ ሊረዷቸው አልቻሉም።

፲፰ ነገር ግን እንዲህ ሆነ ሞዛያ እነርሱ የእርሱን ቋንቋ እንዲማሩ አደረገ። እናም እንዲህ ሆነ በሞዛያ ቋንቋ ከተማሩ በኋላ፣ ዛራሔምላ የአባቶቹን ትውልድ ሐረግ ባስታወሰው መጠን ሰጠ፤ እናም ተጻፉ፣ ነገር ግን በእነዚህ ሰሌዳዎች ውስጥ አይደለም።

፲፱ እናም እንዲህ ሆነ የዛራሔምላና የሞዛያ ህዝብ በአንድነት ᐸተዋሃዱ፤ እናም ᐹሞዛያ ንጉሳቸው ይሆን ዘንድ ተሾመ።

፳ እናም እንዲህ ሆነ በሞዛያ ዘመን፣ በላዩ ላይ የተቀረጸበት ትልቅ ድንጋይ መጣለት፤ እናም ጽሑፉን በእግዚአብሔር ኃይልና ስጦታ ᐸተረጎመው።

፳፩ እናም ኮርያንቱመር ስለሚባል አንድ ሰው ታሪክና ስለህዝቡ ማለቅ ታሪክ ይናገሩ ነበር። እናም ᐸቆሪያንቱመር በዛራሔምላ ህዝብ ተገኝቶ ነበር፤ እርሱም ለዘጠኝ ወራት ያህል ከእነርሱ ጋር ኖረ።

፳፪ አባቶቹን በተመለከተ ደግሞ ትንሽ ቃላት ተናገረ። እናም የመጀመሪያ ወላጆቹ የመጡት ጌታ የህዝቡን ቋንቋ ᐸበቀላ

፲፪ ᐸ ፪ ኔፊ ፭፡፯–፱።
ᐹ ያዕቆ. ፫፡፱።
፲፭ ᐸ ቅ.መ.መ. ዛራሔምላ።
ᐹ ፩ ኔፊ ፫፡፫፣ ፲፱–፳፣ ፭፡፲–፳፪።
፲፭ ᐸ ኤር. ፴፱፡፩–፲፣
ሔሊ. ፳፡፳፩።
ᐹ ሞዛያ ፳፡፪።
፲፯ ᐸ ሞዛያ ፩፡፪–፯።
፲፱ ᐸ ሞዛያ ፳፡፲፫።
ᐹ ኦምኒ ፩፡፲፪።
፳ ᐸ ሞዛያ ፳፡፲፫–፲፱።
ቅ.መ.መ. ባለራዕይ።
፳፩ ᐸ ኤተር ፲፪፡፩።
ቅ.መ.መ. ቆሪያንቱመር።
፳፪ ᐸ ዘፍጥ. ፲፩፡፯–፱፣
ሞዛያ ፳፡፲፣ ፲፯፣
ኤተር ፩፡፴፫።

ቀለበት ጊዜ ^ከግንብ ነው፤ እናም ትክክ
ለኛው የጌታ ቁጣ በፍርዱ መሰረት ወረደ
ባቸው፤ እናም *አጥንታቸው በሰሜናዊው
ምድር ተበትነዋል።

፳፫ እነሆ፣ እኔ አማሌቂ በሞዛያ ዘመን
ተወለድሁ፤ እናም ሞቱን እስከማይ ዘንድ
ኖርሁ፤ እናም ልጁ ^ቢንያም በምትኩ ነገሰ።

፳፬ እናም እነሆ፣ በንጉስ ቢንያም ዘመን
የከፋ ጦርነትና የደም መፋሰስ በኔፋውያ
ንና በላማናውያን መካከል ተመልክቻለሁ።
ነገር ግን እነሆ፣ ኔፋውያን በእነርሱ ላይ ብዙ
ብልጫ አገኙ፤ አዎን፣ እንዲህም ሆኖ ንጉስ
ቢንያም ከዛራሔምላ ምድር አስወጣቸው።

፳፭ እናም እንዲህ ሆነ ማርጀት ጀመ
ርሁ፤ እናም ዘርም ስላልነበረኝና ንጉስ
^ቢንያም በጌታ ፊት ትክክለኛ ሰው መሆ
ኑን ስለማውቅ፣ ስለሆነም፣ ሰዎች ሁሉ ወደ
እስራኤሉ ቅዱስ እግዚአብሔር እንዲመ
ጡና፣ በትንቢትም፣ በራዕይም፣ በመላ
ዕክት አገልግሎትም፣ በልሳን በመናገር
ስጦታም፣ በልሳን መናገርን በማስተርጎም
ስጦታም፣ እንዲሁም ^መልካም በሆኑ ነገ
ሮች ሁሉ እንዲያምኑ በጥብቅ በመምከር
እነዚህን ሰሌዳዎች ለእርሱ *እሰጣለሁ፤
ምክንያቱም ከጌታ ከሚመጣው በስተቀር
መልካም የሆነ ምንም ነገር የለምና፤ እናም
መጥፎ የሆነው ከዲያብሎስ ይመጣል።

፳፮ እናም አሁን፣ የተወደዳችሁ ወንድ
ሞቼ፣ የእስራኤል ቅዱስ ወደ ሆነው ክርስ
ቶስ ^እንድትመጡና፣ የማዳኑን ኃይል እን
ድትካፈሉና፣ የቤዛነቱን ኃይል እንድታገኙ
እፈልጋለሁ። አዎን፣ ወደ እርሱ ኑ፣ እናም
መላ ነፍሳችሁን ለእርሱ እንደ ^መስዋዕት
ነት *አቅርቡ፣ በፀሎታችሁና ^ምስጋናችሁ
ቀጥሉም፣ እስከመጨረሻው ፅኑም፤ እናም
ጌታ ህያው እንደሆነ ትድናላችሁ።

፳፯ እናም አሁን ወደ ኔፊ ምድር ለመመ
ለስ ወደ ምድረበዳው የሄዱትን የተወሰኑ
ሰዎች በሚመለከት በመጠን እናገራለሁ፤
ምክንያቱም የርስት ምድራቸውን ለመው
ረስ የተመኙ ብዙ ሰዎች ነበሩና።

፳፰ ስለሆነም፣ እነርሱ ወደ ምድረበዳው
ሄዱ። እናም መሪያቸው ጠንካራና ኃይ
ለኛ ሰው ነበር፣ እንዲሁም አንገተ ደን
ዳና ሰው ነበር፤ ስለሆነም፣ በእነርሱ መካ
ከል ፀብ እንዲኖር አደረገ፤ እናም በም
ድረበዳ ውስጥ ከሀምሳዎቹ በቀር ሁሉም
^ተገደሉ፣ እናም እንደገና ወደ ዛራሔምላ
ምድር ተመለሱ።

፳፱ እናም እንዲህ ሆነ ሌሎች ቁጥራቸው
ከፍ ያለውን ደግሞ ወሰዱ፣ እናም ወደ
ምድረበዳ እንደገና ጉዞአቸውን ቀጠሉ።

፴ እናም እኔ አማሌቂ፣ ከእነርሱ ጋር የሄደ
ወንድም ነበረኝ፤ እናም እነርሱን በተመለ
ከተ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አላውቅም። ወደ
መቃብሬም መውረዴ ነው፤ ^እነዚህ ሰሌዳ
ዎችም ሙሉ ናቸው። እናም ንግግሬን አበ
ቃለሁ።

የሞርሞን ቃላት

*ሞርሞን የኔፊን ትልቁን ሰሌዳ አሳጠረ—
ትንሹን ሰሌዳ ከሌላኛው ሰሌዳ ጋር አስ
ቀመጠ—ንጉስ ቢንያም በምድሪቱ ውስጥ
ሰላምን መሰረተ። በ፫፻፸፭ ዓ.ም. ገደማ።*

፳፪ለ ኤተር ፩፡ ፩–፭።
ሐ ሞዛያ ፰፡ ፰።
፳፫ሀ ቃላት ፩፡ ፫።
፳፭ሀ ቃላት ፩፡ ፲፯–፲፰፤
ሞዛያ ፳፱፡ ፲፫።
ለ አልማ ፭፡ ፴፣
ኤተር ፬፡ ፲፪፣
ሞሮኒ ፯፡ ፲፭–፲፯።
ሐ ቃላት ፩፡ ፲።
፳፯ሀ ያዕቆ. ፩፡ ፲፣
አልማ ፳፱፡ ፪፣
ሞሮኒ ፲፡ ፴፪።
ለ ፫ ኔፊ ፱፡ ፳።
ሐ ቅ.መ.መ. መስዋዕት።
መ ቅ.መ.መ. ጾም፣ መጸም።
፳፰ሀ ሞዛያ ፱፡ ፩–፪።
፴ሀ ፩ ኔፊ ፯።

፩ እናም አሁን እኔ ᵐሞርሞን ለልጄ ሞሮኒ የፃፍኩትን ታሪክ ለመስጠት እየተዘጋጀሁ እያለሁ፣ እነሆ፣ የህዝቤን የኔፋውያንን በሙሉ የመጥፋትን ምስክር ሆኛአለሁ።

፪ እናም እነዚህን መዛግብት ለልጄ የሰጠሁት ክርስቶስ ከመጣ ᵐከብዙ መቶ ዓመታት በኋላ ነው፤ እርሱም የህዝቡን ፈፅሞ መጥፋት ይመሰክራል ብዬ አስባለሁ። ነገር ግን አንድ ቀን እነርሱን ᵃእንዲጠቅማቸው ዘንድ፣ እነርሱን በተመለከተ እናም ክርስቶስን በተመለከተ ጥቂት ይፅፍ ዘንድ እግዚአብሔር ከእርሱ እንዲድን ይፍቀድ።

፫ እናም አሁን፣ የፃፍኩትን በተመለከተ በመጠን እናገራለሁ፤ አማሌቂ ስለተናገራቸው ᵐከኔፊ ሰሌዳዎች ጀምሮ እስከ ንጉስ ቢንያም ድረስ፣ ያሉትን ᵃአሳጥሬ ከፃፍኩ በኋላ፣ የተሰጠኝን ᵃመዝገብ መረመርሁ፣ እናም ከያዕቆብ እስከ ንጉስ ᵐቢንያም ንግስና ድረስ ትንሹን የነቢያት ታሪክ የያዙትን እነዚህን ሰሌዳዎችና ደግሞ ብዙዎቹን የኔፊን ቃላት አገኘሁ።

፬ እናም በእነዚህ ሰሌዳዎች ላይ ያሉት ነገሮች እኔን ᵐያስደስቱኛል፣ ምክንያቱም የክርስቶስን መምጣት ስለሚተነብዩ፤ እናም አባቶቼ ብዙዎቹ እንደተፈፀሙ ያውቃሉ፤ አዎን፣ እናም ደግሞ እስከአሁን ድረስ ብዙ ነገሮች እኛን በተመለከተ የተተነበዩት እንደተፈፀሙና ከዚያ በኋላ የሚሆኑትም ብዙዎችም በእርግጥ መፈፀም እንዳለባቸው አውቃለሁ—

፭ ስለሆነም፣ በእነርሱ ላይ ምዝገባዬን ለመጨረስ ᵐእነዚህን ነገሮች መረጥሁ፣ ቀሪውን ታሪክ ᵃከኔፊ ሰሌዳዎች ላይ እወስዳለሁ፣ እናም ህዝቤን በተመለከቱ ነገሮች ᵃመቶኛውን መፃፍ አልችልም።

፮ ነገር ግን እነሆ፣ ትንቢቶችንና ራዕዮችን የያዙትን እነዚህን ሰሌዳዎች እወስዳለሁ፣ እናም ከቀሪው ፅሁፌ ጋር አስቀምጣቸዋለሁ፣ ለእኔ ምርጥ ናቸውና፤ እናም ለወንድሞቼ ምርጥ እንደሚሆኑ አውቃለሁ።

፯ እናም ይህን ᵐለብልህ ዓላማ አደርገዋለሁ፤ በእኔ ውስጥ ያለው የጌታ መንፈስ በዝግታ ድምፅ ተናግሮኛልና። እናም አሁን፣ ሁሉንም ነገሮች አላውቅም፤ ነገር ግን ጌታ የሚመጡትን ነገሮች ሁሉ ᵃያውቃል፤ ስለሆነም፣ እንደፈቃዱ ለማድረግ በእኔ ይሰራል።

፰ እናም ወደ እግዚአብሔር ᵐየምፀልየው ወንድሞቼን በተመለከተ ነው፣ ይኸውም እነርሱ አንዴ እንደገና እግዚአብሔርን ወደማወቅ፣ አዎን፣ በክርስቶስ ቤዛነት ይመጡ ዘንድ፤ አንዴ እንደገና ᵃየተወደዱ ህዝቦች ይሆኑ ዘንድ ነው።

፱ እናም አሁን እኔ ሞርሞን፣ ከኔፊ ከወሰድኳቸው ሰሌዳዎች ምዝገባዬን ለመጨረስ እቀጥላለሁ፤ እናም ይህን የማደርገው እግዚአብሔር በሰጠኝ እውቀትና መረዳት መሠረት ነው።

፲ ስለሆነም፣ እንዲህ ሆነ አማሌቂ እነዚህን ሰሌዳዎች ለንጉስ ቢንያም በእጁ ᵐከሰጠው በኋላ፣ ወሰዳቸውና ከትውልድ እስከ ትውልድ እስከ ᵃንጉስ ቢንያም ዘመን ድረስ ለንጉሶች የተላለፉትን ታሪክ ከያዙት ᵃከሌሎች ሰሌዳዎች ጋር አስቀመጣቸው።

፲፩ እናም ከትውልድ ወደ ትውልድ ᵐበእጄ እስከሚገቡ ድረስ ከንጉስ ቢንያም

፩ ፩ ሀ ፲ ኔፊ ፭፡ ፱–፲፪፤ ሞር. ፩፡ ፩–፱፣ ፰፡ ፩፣ ፱–፭። ቅ.መ.መ. ሞርሞን፣ የኔፋውያን ነቢይ።
፪ ሀ ሞር. ፮፡ ፭–፮።
ለ ት. እና ቃ. ፲፡ ፲፮–፳።
፫ ሀ ት. እና ቃ. ፲፡ ፴፰–፴፡ ለ ት. እና ቃ. ፲፡ ፴፭።
ሐ ሞሃያ ፩፡ ፮፣ ሔሌ. ፲፡ ፲፲–፲፭፣ ሞር. ፱፡ ፳፲።
መ ኦሞኒ ፩፡ ፳፲።
፬ ሀ ፩ ኔፊ ፮፡ ፭።
፭ ሀ ይህም በቁጥር ፱ ውስጥ የተጠቀሰው እርሱን የሚያደስት ነገሮች ማለት ነው።
ለ ፩ ኔፊ ፱፡ ፪።
ሐ ፲ ኔፊ ፭፡ ፳–፲፩፣ ፳፮፡ ፮–፲፪።
፯ ሀ ፩ ኔፊ ፱፡ ፭፣ ፲፱፡ ፲፣ ት. እና ቃ. ፲፡ ፲፪–፳፣ ፲፡ ፩–፱፣ ፴፣ ፴፯።
ለ ቅ.መ.መ. ሁሉን የሚያውቅ።
፳ ሀ ፪ ኔፊ ፴፲፡ ፲–፩፣ ኢኖስ ፩፡ ፲፩–፲፪።
ለ ፪ ኔፊ ፴፡ ፮።
፲ ሀ ኦሞኒ ፩፡ ፳፭፣ ፴።
ለ ጄረም ፩፡ ፲፡ ሐ ፩ ኔፊ ፱፡ ፡
፲፩ ሀ ፲ ኔፊ ፭፡ ፳–፲፪፣ ሞር. ፩፡ ፩–፭።

ተላልፈዋል። እናም እኔ ሞርሞን ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እስከሚመጣው እንዲጠበቁ ወደ እግዚአብሔር እፀልያለሁ። እንደሚ ጠበቁም አውቃለሁ፤ ምክንያቱም በተጻ ፈው በእግዚአብሔር ቃል መሰረት ከው ስጣቸው ህዝቦቼና ወንድሞቻቸው በታላ ቁና በመጨረሻው ቀን ^የሚፈረዱባቸው ብዙ ታላቅ ነገሮች በእነርሱ ተፅፈዋልና።

፲፤ እናም አሁን፣ ይህን ንጉስ ቢንያምን በተመለከተ—በህዝቡ መካከል ጥቂት ፀብ ነበረበት።

፲፣ እናም ደግሞ እንዲህ ሆነ የላማናው ያን ወታደሮች ከህዝቡ ጋር ሊዋጉ ^ከኔፊ ምድር ወረዱ። ነገር ግን እነሆ፣ ንጉስ ቢን ያም ወታደሮቹን በአንድ ላይ ሰበሰበ እናም ተቋቋማቸው፤ በገዛ ክንዱ ብርታት በላባን ^ሰይፍ ተዋጋቸው።

፲፪ እናም በጌታ ኃይል ብዙ ሺህ ላማና ውያንን እስከሚገድሉ ድረስ ከጠላቶ ቻቸው ጋር ተጣሉ። እናም እንዲህ ሆነ ከውርስ ምድራቸው ሙሉ በሙሉ እስከ ሚያስወጧቸው ድረስ ከላማናውያን ጋር ተዋጉ።

፲፫ እናም እንዲህ ሆነ ሀሰተኛ ^ክርስቶ ሶች ከነበሩና፣ አፋቸው ከተዘጋና፣ እንደ ወንጀላቸው ከተቀጡ በኋላ፤

፲፬ እናም በህዝቡ መካከል ሀሰተኞቹ ነቢ ያት፣ ሀሰተኛ ሰባኪዎችና መምህራን ከነ በሩ፣ እናም እነዚህ ሁሉ እንደ ወንጀላቸው ከተቀጡ በኋላ፤ እናም ከብዙ ፀብና ብዙ ዎች ተገንጥለው ወደ ላማናውያን የሄዱ ከነበሩ በኋላም፤ እነሆ፣ እንዲህ ሆነ ንጉስ ቢንያም፣ ከህዝቡ መካከል ከነበሩት ቅዱስ ^ነቢያት እርዳታ ጋር—

፲፭ እነሆም ንጉስ ቢንያም ^ቅዱስ ሰው ነበረ፣ እናም በህዝቡም ላይ በፅድቅ ነገሰ፤ ብዙ ቅዱሳን ሰዎች በምድሪቱ ላይ ነበሩም፣ እናም የእግዚአብሔርንም ቃል ^በኃይልና በስልጣን ተናገሩ፤ በህዝብ አንገተ ደንዳ ናነት የተነሳም ብዙ ^ወሳኝ ቃላትን ተጠ ቀሙ—

፲፮ ስለሆነም፣ በቅዱሳን ነቢያት ድጋፍ፣ ንጉስ ቢንያም፣ እናም ነቢያት፣ በሰውነቱ ሙሉ ኃይልና በአከላተ ነፍሱ ሁሉ በመስ ራት፣ በምድሪቱ ላይ አንዴ በድጋሚ ሰላ ምን መሠረተ።

መፅሐፈ ሞዛያ

ምዕራፍ ፩

ንጉስ ቢንያም ለልጆቹ የአባቶቻቸውን ቋንቋ እና ትንቢት አስተማረ—ኃይማኖ ታቸውና ስልጣኔያቸው የተጠበቁት በተ ለያዩ ሠሌዳዎች ላይ በተጠበቁት መዝገቦች ምክንያት ነው—ሞዛያ ለንጉስነት ተመር ጧል እናም መዛግብቱና ሌሎችም ነገሮች አደራ ተሰጥተውታል። ከ፲፱–፲፳፬ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም አሁን የንጉሥ ቢንያም ከሆኑት ህዝቦች ሁሉ መካከል ^በዛራሔምላ ምድር ሁሉ ከዚያ በኋላ ፀብ አልነበረም፣ ስለዚህ ንጉሥ ቢንያም በቀረው ዘመኑ ሁሉ ዘላቂ ሠላም ነበረው።

፲፩ ለ ፪ ኔፊ ፳፭፡፲፰፡ ፳፱፤ ፲፩፤ ፴፫፡፲ ፲፩–፲፭፤ ፫ ኔፊ ፳፯፡ ፳፫–፳፯።
፲፫ ሀ ኦምኒ ፩፡ ፲፪።
ለ ፩ ኔፊ ፡፡ ፱፤ ፪ ኔፊ ፭፡ ፲፡፡፤ ያዕቆ. ፩፡ ፲፤ ሞዛያ ፩፡ ፲፯፤ ት. እና ቃ. ፲፯፡ ፩።
፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. የክርስቶስ ተቃዋሚ።
፲፯ ሀ ኢኖስ ፩፡ ፳፪።
፲፯ ሀ አልማ ፲፫፡ ፳፯።
ለ አልማ ፲፯፡ ፪–፫።
ሐ ሞሮኒ ፱፡ ፡፤ ት. እና ቃ. ፲፳፩፡ ፵፩–፵፫።

[ሞዛያ]
፩ ፩ ሀ ኦምኒ ፩፡ ፲፫።

፪ እናም እንዲህ ሆነ ሦስት ወንዶች ልጆች ነበሩት፤ እናም ስማቸውን ሞዛያና፣ ሔሎሩምና፣ ሔለማን ብሎ ጠራቸው። እናም አስተዋይ ሰዎች ይሆኑ ዘንድና፣ በጌታ እጅ የተሰጣቸውን በአባቶቻቸው አንደበት ስለተነገሩት ትንቢቶች ያውቁ ዘንድ በአባቶቻቸው [ሀ]ቋንቋ ሁሉ [ለ]እንዲ ማሩ አደረገ።

፫ እናም ደግሞ በነህስ ሠሌዳዎች ላይ የተ ቀረፀውን ታሪክ በተመለከተ እንዲህ ሲል አስተማራቸው፥ እነዚህን ታሪኮችና ትዕ ዛዛት የያዙት እነዚህ [ሀ]ሠሌዳዎች ባይኖሩ ኖሮ በአሁኑም ጊዜ እንኳን ቢሆን የእግ ዚአብሔርን ሚስጥር ባለማወቅ [ለ]በድንቁ ርና እንደምንሰቃይ ልጆቼ እንድታስታ ውሱ እፈልጋለሁ።

፬ በእነዚህ ሠሌዳዎች እርዳታ ካልሆነ በቀር አባታችን ሌሂ እነዚህን ሁሉ ነገሮች ለልጆቹ በማስታወስ ለማስተማር አይቻ ለውም ነበር፤ ምክንያቱም የግብፃውያ ንን [ሀ]ቋንቋ የተማረ ስለሆነ እነዚህን ፅሁ ፎች ለማንበብ ይቻለዋል፣ እናም ልጆቹ ልጆቻቸውን ማስተማር ይችሉ ዘንድ ይህ ንኑ ልጆቹን አስተማራቸው፣ እናም ስለ ዚህ እስከዚህ ጊዜም ድረስ የእግዚአብሔ ርን ትዕዛዛት ይፈፅማሉ።

፭ ልጆቹ እንዲህ እላችኋለሁ፥ እኛ የእ ርሱን [ሀ]ሚስጥር [ለ]አንብበን እንገነዘብ ዘንድ በእግዚአብሔር እጅ [ሐ]የተቀመጡትና የተ ጠበቁት እነዚህ ነገሮች፣ እንዲሁም ሁልጊ ዜም ከዐይናችን ስር ያሉት ትዕዛዛቱ ባይኖሩ ኖሮ አባቶቻችንም እንኳን ቢሆኑ እምነት አጥተው ይመነምኑ ነበር፣ እናም ስለእነ ዚህ ነገሮች ምንም እንደማያውቁት፣ ወይም በሚያስተምሩአቸው ጊዜም ስህተት በሆ ነው በአባቶቻቸው [መ]ወግ ምክንያት እንደ ማያምኑት ወንድሞቻችን እንደላማናው ያን እንሆን ነበር።

፮ ልጆቹ ሆይ፣ እነዚህ አባባሎች እው ነት መሆናቸውን፣ እናም ደግሞ እነዚህ መዛግብት [ሀ]እውነት እንደሆኑ እንድታስ ታውሱ እፈልጋለሁ። እናም ኢየሩሳሌምን ለቀው ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ እስከአሁን የአባቶቻችንን አባባሎች መዛግብትን የያዙ የኔፊ ሰሌዳዎችን ደግሞ ተመልከቱ፣ እነ ርሱም እውነተኛ ናቸው፤ እናም እኛ የእ ነርሱን እርግጠኝነት እናውቃለን ምክንያ ቱም እነርሱ በዐይኖቻችን ፊት ቀርበዋል።

፯ እናም አሁን፣ ልጆቼ፣ እናንተ ትጠ ቀሙ ዘንድ እነርሱን በትጋት [ሀ]መፈተሽን አንድታስታውሱ እፈልጋለሁ፤ እናም ጌታ ለአባቶቻችን በገባው [ለ]ቃል ኪዳን መሰረት በምድሪቱ [ሐ]ትበለፅጉ ዘንድ የእግዚአብሔ ርን ትዕዛዛት [መ]እንድትጠብቁ እፈልጋለሁ።

፰ እናም በዚህ መፅሐፍ ያልተፃፉትን በጣም ብዙ ተጨማሪ ነገሮችን ንጉስ ቢን ያም ለልጆቹ አስተማረ።

፱ እናም እንዲህ ሆነ ንጉስ ቢንያም ልጆ ቹን ማስተማር ከጨረሰ በኋላ አረጀ፣ እናም በቅርቡ ምድር ሁሉ ወደሚሄዱበት መሄድ እንዳለበት ተመለከተ፤ ስለዚህ መንግስቱን ከልጆቹ ለአንደኛው ልጁ መስጠት ተገቢ መሆኑን አሰበ።

፲ ስለዚህ፣ ሞዛያን በፊቱ እንዲመጣ አደ ረገ፤ እናም እነዚህ ለእርሱ የተናገራቸው ቃላት ናቸው፥ ልጄ በዚህ ምድር ሁሉ በዚህ ህዝብ ሁሉ ወይም [ሀ]በዛራሔምላ ህዝብ እናም በምድሪቱ በሚኖሩት በሞዛያ ህዝብ መካከል በአንድ ላይ ይሰበሰቡ ዘንድ አዋጅን እንድ ታውጅ እፈልጋለሁ፤ በማግስቱም ጌታ እግ

፪ ሀ ሞር. ፱፡ ፴፪።
ለ ሞዛያ ፡ ፲፡–፲፭፤ ት. እና ቃ. ፰፰፡ ፰፭፣ ፰፰።
፫ ሀ ቅ.መ.መ. ሰሌዳዎች።
ለ አልማ ፴፯፡ ፰–፱።
፬ ሀ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡ ፰፡፡
፭ ሀ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ሚስጥሮች።
ለ ዘዳግ. ፮፡ ፮–፰።
ሐ ቅ.መ.መ. ቅዱሳት መጻህፍት—የሚጠበቁ ቅዱስ መጻፍህት።
መ ሞዛያ ፲፡ ፲፩–፲፯።
፮ ሀ ፩ ኔፊ ፩፡ ፫፤ ፪ ኔፊ ፴፫፡ ፲–፲፩፤ ሞሮኒ ፣ ፡ ፰፣።
፯ ሀ ቅ.መ.መ. ቅዱሳት መጻህፍት።
ለ አልማ ፱፡ ፲፪–፲፱።
ሐ መዝ. ፻፳፪፡ ፣ ፤ ፩ ኔፊ ፪፡ ፰።
መ ሞዛያ ፪፡ ፰፪፤ አልማ ፣ ፡ ፰–፰፪።
፲ ሀ ኦምኒ ፩፡ ፲፡፡

ዚአብሔር ለእኛ በሰጠን በዚህ ህዝብ ላይ አንተ ^ንጉስና ገዢ መሆንህን በራሴ አንደ በት ለህዝቤ አስታውቃለሁ።

፲፩ እናም ከዚህ በተጨማሪ፣ ጌታ እግዚ አብሔር ከኢየሩሳሌም ምድር ካወጣቸው ህዝቦች መካከል ይለዩ ዘንድ ለዚህ ህዝብ ᵛስም እሰጣለሁ፤ እናም ይህንን የማደርገው እነርሱ የጌታን ትዕዛዛት በመጠበቅ ትጉህ ስለነበሩ ነው።

፲፪ እናም ᵛበመተላለፍ ካልሆነ በቀር ሊደ መሰስ የማይችል ስም እሰጣቸዋለሁ።

፲፫ አዎን፣ እናም በተጨማሪ እልሀለሁ፥ እነዚህ እጅግ በጌታ የተወደዱ ሰዎች ወደ ᵛመተላለፍ ቢወድቁ፣ እናም ኃጢአተኞ ችና፣ ዝሙትን አድራጊዎች ቢሆኑ፤ ጌታ አሳልፎ ይሰጣቸዋል፣ በዚህም እንደ ወን ድሞቻቸውም ^ደካሞች ይሆናሉ፤ እናም ከዚህ ቀደም አባቶቻችንን እንዳዳናቸው ወደር በሌለውና ድንቅ ሃይሉ ከእንግዲህ ^አያድናቸውም።

፲፬ እንዲህም እልሀለሁ፣ ለአባቶቻችን ባደረገው ጥበቃ እጁን ባይዘረጋ ኖሮ እነ ርሱ በላማናውያን እጅ በወደቁ እናም በጥላ ቻቸው ተጎጂ በሆኑ ነበር።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ ንጉስ ቢንያም ለልጁ ንግግሩን ከጨረሰ በኋላ፣ የንግስ ታቱን አገዛዝ የተመለከቱ ጉዳዮችን ሁሉ በኃላፊነት ሰጠው።

፲፮ እናም በተጨማሪ፣ ደግሞ ᵛበነህስ ሰሌዳዎች ላይ የተፃፉትን ታሪኮች በተመ ለከተ፣ እናም ደግሞ የኔፊን ስሌዳዎች በተ መለከተና፣ ደግሞ የላባንን ^ሳንጃ፣ እን ዲሁም እያንዳንዳቸው ለእርሱ በሚሰ ጡት ትኩረትና ትጋት መሰረት ይመሩበት ዘንድ በጌታ እጅ የተዘጋጀውን አባቶቻቸ ውን ከምድረበዳ የመራውን ^ኳሱን ወይም መሪውን ኃላፊነት ሰጠው።

፲፯ ስለዚህ፣ እምነት ባጡበት ጊዜ በጉዞአ ቸው አልበለፀጉም ወይም እድገትንም አላ ገኙም ነበር፣ ነገር ግን ᵛወደኋላ ተወስደው ነበር፣ እናም የእግዚአብሔርን መከፋት በእ ነርሱ ላይ አመጣባቸው፤ እናም ስለዚህ ሀላ ፊነታቸውን እንዲያስታውሱ ለማነሳሳት በረ ሃብና በቁስል መቅሰፍት ተመተው ነበር።

፲፰ እናም አሁን፣ እንዲህ ሆነ ሞዛያ ሔደና፣ አባቱ እንዳዘዘው አደረገ፤ እናም በዛራሔምላ ምድር ላሉት ህዝቦች ሁሉ ወደ ቤተ መቅደሱ በመሄድ አባቱ የሚናገረውን ቃላት እንዲያደምጡ በአንድ ላይ ይሰበሰቡ ዘንድ አወጀላቸው።

ምዕራፍ ፪

ንጉስ ቢንያም ለህዝቡ ንግግር አደ ረገ—የንግስናውን ፍትሀዊነት፣ ተገቢ ነት፣ እና መንፈሳዊነት ገለፀ—የሰማ ዩን ንጉሳቸውን እንዲያገለግሉ መከራ ቸው—በእግዚአብሔር ላይ የሚያምፁ በማይጠፋው እሳት አይነት ጭንቀት ይሰ ቃያሉ። ፣ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ ሞዛያ አባቱ እንዲ ያደርግ እንዳዘዘው ከፈጸመና፣ በምድሪቱ ሁሉ ላይ አዋጅን ካደረገ በኋላ፣ ንጉስ ቢን ያም የሚነግራቸውን ቃላት ለማዳመጥ ወደ ቤተ መቅደሱ ለመምጣት ህዝቡ በምድሪቱ ሁሉ በአንድ ላይ ተሰበሰቡ።

፪ እናም እጅግ በርካታ እንዲያውም በጣም በዝተው ስለነበረ አልቆጠሯቸውም ነበር፤ ምክንያቱም በምድሪቱ ላይ በእጅግ ተባዝተውና በጣም ታላቅ ሆነው ነበርና።

፫ እናም ደግሞ በሙሴ ህግ ᵛመሰረት ^መስዋዕት ያቀርቡ ዘንድ፣ እናም ^መስ ዋዕቱን ያቃጥሉ ዘንድ ከመንጋዎቻቸው ᵛየመጀመሪያውን አመጡ፤

፲ ለ ሞዛያ ፪፡ ፴።
፲፩ ሀ ሞዛያ ፩፡ ፳–፲፪።
፲፪ ሀ ቅ.መ.መ. ኃጢያት።
፲፫ ሀ ዕብ. ፯፡ ፱–፯።
ለ ሔለ. ፱፡ ፳፱–፳፯።
ሐ ት.እና ቃ. ፲፫፡ ፳–፲።
፲፯ ሀ ሞዛያ ፩፡ ፫።
ለ ፩ ኔፊ ፱፡ ፳–፲፱፤ ቃላት ፩፡ ፲፫፤ ት.እና ቃ. ፲፯፡ ፩።
ሐ ፩ ኔፊ ፲፯፡ ፲።
፲፯ ሀ ፩ ኔፊ ፲፳፡ ፲፪–፲፫።
፪ ፫ ሀ ፪ ኔፊ ፳፭፡ ፳፱፤ አልማ ፴፡ ፫፤ ፴፱፡ ፲፫–፲፱።
ለ ቅ.መ.መ. መስዋዕት።
ሐ ፩ ኔፊ ፭፡ ፱።
መ ዘፍጥ. ፱፡ ፱።

፬ እናም ደግሞ ከኢየሩሳሌም ምድር ላወጣቸውና፣ ከጠላቶቻቸው እጅ ላዳና ቸውን፣ እንዲሁም [ሀ]አስተማሪዎቻቸው ይሆኑ ዘንድ ትክክለኛ ሰዎችን [ለ]ለሾመላ ቸው፣ እናም ደግሞ [ሐ]በዛራሔምላ ምድር ሰላምን የመሰረተውንና፣ ሰዎች ሁሉ እን ዲደሰቱና በእግዚአብሔርና በሁሉም ሰዎች [መ]ፍቅር እንዲሞሉ የእግዚአብሔርን ትዕዛ ዛት [ሠ]እንዲጠብቁ ያስተማራቸውን ጻድቅ ሰው የእነርሱ ንጉስ እንዲሆን ላደረገው ለጌታ አምላካቸው ደግሞ ምስጋናን ያቀርቡ ዘንድ የሚሰውአቸውን መንጋዎች አመጡ።

፭ እናም እንዲህ ሆነ ወደ ቤተመቅደሱ በመጡ ጊዜ፣ ማናቸውም [ሀ]በየቤተሰቦቻ ቸው ሚስቱን፣ ወንድ ልጆቹንና፣ ሴት ልጆቹን እናም ወንድና ሴት ልጆቻቸውን፣ ከታላቁ እስከ ታናሹ፣ ለእያንዳንዱ ቤተ ሰብ የሆነ በዙሪያው ተለያይተው ድንኳና ቸውን ተከሉ።

፮ እናም ንጉስ ቢንያም ለእነርሱ የሚናገረ ውን [ለ]ድንኳኑ ውስጥ ተቀምጠው ያደምጡ ዘንድ፣ እያንዳንዱ ሰው የድንኳኑን መዝጊያ ወደ ቤተ መቅደሱ በማድረግ በቤተ መቅ ደሱ ዙሪያ ድንኳናቸውን ተከሉ፤

፯ ህዝቡ በጣም ብዙ ስለነበሩ ንጉስ ቢን ያም በመቅደሱ አጥር ዙሪያ ሁሉንም ለማ ስተማር አልቻለም፤ ስለዚህ ህዝቡ እርሱ የሚናገራቸውን ቃላት ያደምጡ ዘንድ ሰገ ነት እንዲቆም አደረገ።

፰ እናም እንዲህ ሆነ በሰገነት ላይ ሆኖ ለህዝቡ መናገር ጀመረ፤ እናም ህዝቡ ብዙ በመሆኑ ሁሉም ሊሰሙት አልቻሉም፤ ስለ ዚህ ድምፁን ባልሰሙት ቃሉንም ደግሞ ይቀበሉት ዘንድ፣ የተናገራቸው ቃላት እን ዲፃፉና በመካከላቸው እንዲላክ አደረገ።

፱ እናም እርሱ [ሀ]የተናገራቸው እናም እን ዲፃፉ ያደረጋቸው ቃላት እነዚህ ናቸው፥ በዚህ ቀን ለእናንተ ስናገር ቃሌን ማዳመጥ የቻላችሁ እናንተ በአንድነት የተሰበሰባችሁ ወንድሞቼ፤ የምናገራቸውን ቃላት [ለ]በከንቱ እንድትመለከቷቸው ዘንድ ወደእዚህ እን ድትመጡ አላዘዝኳችሁም፣ ነገር ግን እኔን [ሐ]አዳምጡ፣ እናም ትሰሙኝ ዘንድ ጆሮአ ችሁን፣ ትረዱኝ ዘንድም [መ]ልባችሁን፣ የእ ግዚአብሔርም [ሠ]ሚስጥር ዓላማው ይገለ ጥላችሁ ዘንድም [ረ]አዕምሮአችሁን ክፈቱ።

፲ እኔን [ሀ]እንድትፈሩኝ ወይም እኔንም ከሚች ሰው የበለጠ አድርጋችሁ እንድታ ስቡኝ ዘንድ ወደዚህ እንድትመጡ አላዘ ዝኳችሁም።

፲፩ ነገር ግን እኔ እንደ እናንተው ነኝ፣ በሁሉም አይነት የሰውነትና የአዕምሮ ጉስ ቁልና ስር የሆንኩ፤ ይሁን እንጂ በዚህ ህዝብ ተመርጫለሁ፣ በአባቴም ተቀብቻ ለሁ፣ በዚህ ህዝብ ላይ ገዢና ንጉስ እንድሆ ንም በጌታ እጅ ተፈቅዶልኛል፣ እናም ጌታ በሰጠኝ በሙሉ ኃይል፣ አዕምሮና፣ ብር ታት እናንተን እንዳገለግል ወደር በሌለው ኃይሉ ተቀምጫለሁ፣ እንዲሁም ተጠብቄ አለሁ።

፲፪ እንዲህ እላችኋለሁ እስካሁን ድረስ እንኳን ጊዜዬን እናንተን በማገልገል እንዳ ጠፋ ተፈቅዶልኛል፣ እናም [ሀ]ወርቅም ሆነ፣ ብር ባለፀጋ የሚያደርግ ማንኛውንም አይ ነት ነገር ከእናንተ አልፈለግሁም፤

፲፫ እናንተ በግዞት እንድትቀመጡ፣ ወይም አንዳችሁ ለአንዳችሁ ባርያ እንድ ትሆኑ፣ ወይም እንድትገድሉ፣ ወይም እን ድትዘርፉ፣ ወይም እንድትሰርቁም፣ ሆነ ዝሙትን እንድትፈፅሙ አልፈቀድኩም፤ ወይም ምንም ዓይነት ኃጢያት እንድት ፈፅሙ አልፈቅድኩም፣ እናም በሁሉም

፩ *ሀ* ሞዛያ ፲፰፡፲፰–፳፪። ቅ.መ.መ. ማስተማር፣ አስተማሪ።
ለ ቅ.መ.መ. ጥሪ፣ በእግዚአብሔር መጠራት፣ የተጠራበት።
ሐ ኦምኒ ፩፡ ፲፪–፲፭።
መ ቅ.መ.መ. ፍቅር።
ሠ ዮሐ. ፲፭፡ ፲።
፭ *ሀ* ቅ.መ.መ. ቤተሰብ።
፮ *ሀ* ዘፀአ. ፴፫፡ ፳–፲።
፱ *ሀ* ሞዛያ ፳፡ ፲።
ለ ት.እና ቃ. ፮፡ ፲፪።
ሐ ቅ.መ.መ. ማዳመጥ።
መ ሞዛያ ፲፪፡ ፳፯፣ ፲ ኔፊ ፲፱፡ ፴፲።
ሠ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ሚስጥሮች።
ረ ቅ.መ.መ. አዕምሮ።
፲ *ሀ* ቅ.መ.መ. ፍርሀት።
፲፪ *ሀ* የሐዋ. ፳፡ ፴፲–፴፭።

ነገር እንዳዘዛችሁ የጌታን ትዕዛዛት እንድ
ትጠብቁ አስተምሬአችኋለሁ—

፲፬ እናም እኔ ራሴ፣ እናንተን ᵐአገለግል
ዘንድና፣ ቀረጥ እንዳይከብድባችሁ፣ እናም
ልትቋቋሙት የማይቻል ፅኑ የሆነ ምንም
ነገር በእናንተ ላይ አንዳይመጣባችሁ ዘንድ
በእጄ ሰርቻለሁ—እናም እኔ ለተናገርኳ
ችሁ ለእነዚህ ነገሮች ሁሉ በዚህ ቀን እና
ንተ ራሳችሁ ምስክር ናችሁ።

፲፭ ሆኖም ወንድሞቼ፣ እነዚህን ነገሮች
ለጉራ አይደለም ያደረግኋቸው፣ ወይም
እነዚህን ነገሮች የነገርኳችሁ እናንተን ለመ
ውቀስ አይደለም፣ ነገር ግን በዚህ ቀን በእ
ግዚአብሔር ፊት በንጹህ ᵐህሊና መመለስ
መቻሌን ታውቁ ዘንድ እነዚህን ነገሮች እነ
ግራችኋለሁ።

፲፮ እነሆ፣ እላችኋለሁ ዘመኔን እናን
ተን በማገልገል አሳልፌአለሁ ስላልኳችሁ
መኩራት አልፈልግም፣ በእውነት በእግ
ዚአብሔርም አገልግሎት ላይ ነበርኩና።

፲፯ እናም እነሆ፣ እናንተ ᵐጥበብን ትማሩ
ዘንድ፤ እናንተ ᵃሰዎችን ᵇበምታገለግሉ
በት ጊዜ እግዚአብሔርን ብቻ እያገለገላ
ችሁ እንደሆነ እንድትማሩ ዘንድ እነዚህን
ነገሮች እናገራችኋለሁ።

፲፰ እነሆ፣ የእናንተ ንጉስ ብላችሁ ጠር
ታችሁኛል፣ እናንተ ንጉስ ብላችሁ የም
ትጠሩኝ እኔ እናንተን ᵐለማገልገል ከሰ
ራሁ፣ እናንተስ እርስ በራሳችሁን ለማገ
ልገል መስራት አይገባችሁምን?

፲፱ እናም እነሆ ደግሞ፣ ዘመኑን ᵐእና
ንተን በማገልገል የሚያሳልፈው፣ የእና
ንተ ንጉስ ብላችሁ የምትጠሩኝ፣ እናም
አሁንም አምላክን የማገለግለው፣ ከእና
ንተ ምስጋና የሚገባኝ ከሆንኩኝ፣ አቤቱ
ምን ያህል የሰማይን ንጉሳችሁን ማመስ
ገን ይገባችኋል!

፳ ወንድሞቼ እላችኋለሁ፣ እናንተን ለፈ
ጠረውም፣ ለጠበቀውና ላዳነውም፣ እን
ድትደሰቱ ላደረገውም፣ እንዲሁም እርስ
በእርሳችሁ በሰላም እንድትኖሩ ለረዳችሁ
ᵐእግዚአብሔር ነፍሳችሁ ያለውን ሁሉንም
ምስጋና እና ᵃውዳሴ ብትሰጡ—

፳፩ እንዲህ እላችኋለሁ ከመጀመሪያ
ጀምሮ የፈጠራችሁና፣ ᵐእንደፈቃዳችሁ
ትኖሩና ትንቀሳቀሱ፣ እናም ትሰሩ ዘንድ
እስትንፋሱን በመስጠት ከቀን ቀን የጠበቃ
ችሁን፣ እናም ከአንዱ ወቅት ወደ ሌሊኛው
እንኳን የደገፋችሁን የምታገለግሉ ከሆነ፣
እላችኋለሁ፣ በሙሉ ነፍሳችሁ እርሱን የም
ታገለግሉ ብትሆኑም ᵃየማትጠቅሙ ባሪያ
ዎች ትሆናላችሁ።

፳፪ እናም እነሆ፣ እርሱ ከእናንተ የሚ
ፈልገው ሁሉ ᵐትዕዛዛቱን ᵃእንድትጠብቁ
ነው፤ እናም እናንተ ትዕዛዛቱን የምትጠ
ብቁ ከሆነ በምድሪቱ እንደምትበለፅጉ ቃል
ገብቷል፤ እናም ከተናገረው ᵇየተለየ ነገር
አያደርግም፤ ስለዚህ፣ ትዕዛዛቱን ᶜየምት
ጠብቁ ከሆነ እርሱ ይባርካችኋልም ያበለ
ፅጋችኋልም።

፳፫ እናም አሁን፣ በመጀመሪያ ፈጥሯች
ኋል፣ ህይወታችሁንም ሰጥቷችኋል፣ ለእ
ዚህም እናንተም ለእርሱ እዳ አለባችሁ።

፳፬ እናም ሁለተኛ፣ እርሱ እንዳዘዛችሁ
እንድታደርጉ ይፈልጋል፤ እናንተም የም
ታደርጉት ከሆነ ወዲያው ᵐይባርካችኋል፤
ስለዚህም ከፍሎአችኋል። እና አሁንም እና
ንተ በእርሱ እዳ አላችሁ፤ እናም ከዘለዓለም
እስከዘለዓለም አላችሁም፣ ይኖራችኋልም፤
ስለሆነም፣ በምን ትኮራላችሁ?

፲፬ ᵐ ፩ ቆሮ. ፱፡ ፲፰።
፲፭ ᵐ ቅ.መ.መ. ህሊና።
፲፯ ᵐ ቅ.መ.መ. ጥበብ።
ᵃ ቅ.መ.መ. እህት፤ ወንድሞች፣ ወንድም።
ᵇ ማቴ. ፳፫፡ ፰፣ ፳፡ ፳፫–፳፭። ቅ.መ.መ. አገልግሎት።
፲፰ ᵐ ማቴ. ፳፡ ፳፮–፳፯።
፲፱ ᵐ ቅ.መ.መ. አመስጋኝ፣ ምስጋናን፣ ምስጋና መስጠት።
፳ ᵐ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ።
ᵃ ፩ ኔፊ ፲፰፡ ፲፯።
፳፩ ᵐ ቅ.መ.መ. ነጻ ምርጫ።
ᵃ ሉቃ. ፲፯፡ ፯–፲።
፳፪ ᵐ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ትእዛዛት።
ᵃ ዘሌዋ. ፳፭፡ ፲፰–፲፱፣ ፪ ኔፊ ፭፡ ፱።
ᵇ ት. እና ቃ. ፫፡ ፭–፪።
ᶜ ት. እና ቃ. ፲፡ ፯፣ ፹፰፡ ፪–፫።
፳፫ ᵐ ቅ.መ.መ. መባረክ፣ የተባረከ፣ በረከት።

፳፭ እናም አሁን ስለራሳችሁ መናገር የምትችሉት አለን? ብዬ እጠይቃለሁ፣ እኔ የለም ብዬ እመልስላችኋለሁ። እናም እናንተ ከምድር ትቢያ እኩል ነን ለማለት አትችሉም፤ ይሁን እንጂ እናንተ ከምድር [ሀ]ትቢያ ነው [ለ]የተፈጠራችሁት፤ እነሆ ያም የእርሱ፣ እናንተን የፈጠረው ነው።

፳፮ እናም በተለይ፣ እናንተ ንጉስ ብላ ችሁ የምትጠሩኝ እኔ ከእናንተ የተሻልኩ አይደለሁም፤ እኔም ደግሞ ከአፈር የተፈ ጠርኩ ነኝና። እናም እንደምታዩኝ አርጅቻ ለሁም ወደመጣሁበት እናት ምድር ልመ ለስም ተቃርቤአለሁ።

፳፯ ስለዚህ፣ እንዳልኳችሁ በእግዚአብ ሔር ፊት በንጹህ ህሊና [ሁ]በመራመድ እና ንተን አገልግያለሁ፤ ቢሆንም እኔ በዚህ ጊዜ እናንተን በተመለከተ እግዚአብሔር ባዘዘኝ ነገሮች እንዲፈረድብኝ በምቆምበት ጊዜ እንከን የለሽ ሆኜ እንድገኝ፣ እናም [ለ]ደማችሁ በእኔ ላይ እንዳይመጣ፣ እና ንተን በአንድ ላይ እንድትሰበሰቡ አድ ርጌአለሁ።

፳፰ እላችኋለሁ ወደመቃብሬ ልወ ርድ ባልኩበት በዚህ ጊዜ በሰላም እወ ርድ ዘንድ፣ የማይሞተው [ሂ]መንፈሴ ትክ ክለኛውን አምላክ ለማመስገን [ለ]ከመዘም ራን ጋር ይገኝ ዘንድ፣ ደችሁን ከልብሴ ላይ [ሐ]አፀዳው ዘንድ፣ ራሳችሁን በአንድ ላይ እንድትሰበስቡ አደረግሁ።

፳፱ እናም በተጨማሪ፣ ከእንግዲህ የእና ንተ አስተማሪም ሆነ ንጉስ መሆን አለመ ቻሌን እነግራችሁ ዘንድ በአንድ ላይ እን ድትሰባሰቡ አድርጌአለሁ።

፴ በዚህ ጊዜ እንኳን፣ ለእናንተ ለመናገር በምሞክርበት ጊዜ ሰውነቴ በሙሉ እጅግ ይንቀጠቀጣል፣ ነገር ግን ጌታ እግዚአብ ሔር ይረዳኛል፤ እናም ለእናንተ እንድ ናገር ፈቅዶልኛል፣ ልጄ ሞዛያ በእናንተ ላይ ንጉስና ገዢ መሆኑን በዚህ ቀን ለእና ንተ እንዳውጅም አዝዞኛል።

፴፩ እናም አሁን፣ ወንድሞቼ፣ እስካ ሁን እንዳደረጋችሁት ሁሉ እንድታደርጉ እፈልጋለሁ። ትዕዛዛቴንና፣ ደግሞ የአባ ቴን ትዕዛዛት እንደጠበቃችሁና፣ እንደበ ለፀጋችሁ፣ እንዲሁም በጠላቶቻችሁ እጅ ከመውደቅ እንደተጠበቃችሁ፣ በተመሳ ሳዩም የልጄን ትዕዛዛት ወይም እርሱ ለእ ናንተ የሚሰጣችሁን የእግዚአብሔርን ትዕ ዛዛት ከጠበቃችሁ፣ በምድሪቱ ላይ ትበለፅ ጋላችሁ፣ እናም ጠላቶቻችሁ በእናንተ ላይ ኃይል አይኖራቸውም።

፴፪ ነገር ግን ህዝቤ ሆይ በመካከላችሁ [ሀ]ፀብ እንዳይነሳ፣ እና በአባቴ በሞዛያ የተ ነገሩትን እርኩስ መንፈስ ለመታዘዝ ከመ ምረጥ ተጠንቀቁ።

፴፫ እነሆም፣ ያንን መንፈስ ሰምቶ ለመ ቀበል ለመረጠው ወዮለት፣ እርሱን ለመ ስማት ከመረጠ፣ እናም በኃጢአቱ ከቀረ፣ እናም ከሞተ፣ እርሱም ለነፍሱ [ሁ]ኩነኔን ይጠጣል፤ ከራሱ እውቀት ጋርም ተፃራሪ በመሆን የእግዚአብሔርን ህግ በመተላለፉ ለስራው [ለ]ዘለዓለማዊ ቅጣትን እንደ ደሞዙ ይቀበላልና።

፴፬ እንዲህ እላችኋለሁ፣ ስለእነዚህ ነገ ሮች ከትናንሽ ልጆቻችሁ በስተቀር ከእና ንተ መካከል ማንም ያልተማረ፣ ነገር ግን እናንተ ለሰማዩ አባታችሁ ያላችሁን ሁሉና ራሳችሁንም ለእርሱ ለመስጠት ለዘለዓለም እዳ እንዳላችሁ የማያውቅ፣ እናም ደግሞ በቅዱሳን ነቢያት አባታችን ሌሂ ኢየሩሳሌ ምን ለቆ እስከወጣ ድረስ የተነገሩትን ትን ቢቶችን የያዙትን መዛግብት በተመለከተ ያልተማረ ማንም የለም፤

፴፭ ደግሞም፣ እስከ አሁን ድረስ በአባ ቶቻችን የተነገሩት ሁሉ ያልተማረ ማንም የለም። እናም እነሆ፣ ደግሞ ነቢያቱ የተና

፳፭ *ሀ* ዘፍጥ. ፫፡፲፱፤ ያዕቆ. ፪፡፳፭። *ለ* ቅ.መ.መ. መፍጠር፣ ፍጥረት።

፳፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. መራመድ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መራመድ (መሄድ)። *ለ* ያዕቆ. ፩፡፲፱።

፳፰ *ሀ* ቅ.መ.መ. መንፈስ። *ለ* ሞር. ፯፡፯።

ሐ ያዕቆ. ፪፡፪።

፴፪ *ሀ* ፫ ኔፊ ፲፯፡፳፭–፴። ፴፫ *ሀ* ቅ.መ.መ. ኩነኔ። *ለ* ት.እና ቃ. ፲፱፡፭፣ ፲–፲፪።

ገሩት በጌታ የታዘዙትን ነበር፤ ስለዚህ ትክ ክል እና እውነተኛ ናቸው።

፴፤ እናም አሁን፣ ወንድሞቼ እላችኋ ለሁ፣ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ካወቃችሁና ከተማራችሁ በኋላ እናንተ የምትተላለፉና ከተነገረው በተቃራኒ የምትሄዱ ከሆነ፣ ከጌታ መንፈስ ራሳችሁን አርቃችሁ፣ ትባ ረኩበት፣ ትበለፅጉበት፣ እናም ትጠበቁ በት ዘንድ በጥበብ ጎዳና እናንተን እንዲ መራ ቦታ አይኖረውም—

፴፭ እላችኋለሁ፣ ይህንን የሚያደርገው ሰው፣ ከእግዚአብሔር ጋር ተቃራኒ በመ ሆን [ሀ]በአመፃ ይመጣል፤ ስለዚህ እርኩስ መንፈስን ለመስማት ይመርጣል፣ እናም ለፅድቅ ሁሉ ጠላት ይሆናል፤ ስለዚህ ጌታ በእርሱ ውስጥ ሥፍራ አይኖረውም፣ ምክ ንያቱም እርሱ [ለ]ቅዱስ ባልሆኑ ቤተመቅደ ሶች ውስጥ አይኖርምና።

፴፮ ስለዚህ ያ ሰው [ሐ]ንስሀ ካልገባ፣ እናም ለእግዚአብሔር ጠላት እንደሆነ ቀርቶ ቢሞት፣ መለኮታዊ የሆነው ትክክለኛው [መ]ፍትህ ዘለዓለማዊ የሆነውን ነፍሱን ሀይ ለኛ የሆነ [ሠ]የጥፋተኛነት ስሜት ይቀሰቅሰ ዋል፤ እርሱንም በጌታ ፊት ያሸማቅቀዋል፣ እናም ደረቱን ነበልባሉ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ከፍ እንደሚል ልክ እንደማይጠ ፋው እሳት በጥፋተኝነትና፣ በህመም፣ እን ዲሁም በጭንቀት ይሞላዋል።

፴፯ እናም አሁን እላችኋለሁ፣ [ረ]ምህረት ለዚያ ሰው ምንም ሥፍራ አይኖራትም፤ ስለዚህ የመጨረሻ ዕጣው ማለቂያ የሌለ ውን ቅጣት መጋፈጥ ነው።

፴ ቃሌን የምትረዱ እናንተ ሽማግሌዎ ችና፣ ደግሞ እናንተ ወጣቶች፣ ደግሞም እናንተ ትናንሽ ልጆች፣ እናንተ ትረዱት ዘንድ በግልፅ ተናግሬአለሁና፣ ወደ መተ ላለፍ የወደቁትን አሰቃቂ ሁኔታ ነቅታችሁ [ሰ]እንድታስታውሱ እፀልያለሁ።

፴፩ እናም በተጨማሪ፣ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት የሚጠብቁትን የተባረከና [ሸ]አስደ ሳቹን ሁኔታ እንድትገነዘቡ እፈልጋለሁ። እነሆም እነርሱ በሁሉም ነገሮች፣ ለጊዜ ያዊም ሆነ ለመንፈሳዊ፣ [ቀ]የተባረኩ ናቸ ውና፤ እናም እስከ መጨረሻው [በ]ታማኝ ነት ከዘለቁ፣ ለዘለአለም በማያልቀው ደስታ ከእግዚአብሔር ጋር ይኖሩ ዘንድ፣ መንግ ስተ [ተ]ሰማይ ትቀበላቸዋለች። አቤቱ አስ ታውሱ፤ እነዚህ ነገሮች እውነት መሆናቸ ውን አስታውሱ፣ ምክንያቱም ጌታ እግዚ አብሔር ተናግሮታልና።

ምዕራፍ ፫

ንጉስ ቢንያም ንግግሩን ቀጠለ—ሁሉን የሚገዛው ጌታ በጭቃ ሰውነቱ በሰዎች መካከል ያገለግላል—ለዓለም ኃጢአቶች ዋጋን ሲከፍል ደም ከሰውነቱ ቀዳዳ ሁሉ ይፈሳል—ደህንነት የሚመጣበት ብቸ ኛው ስም የእርሱ ነው—ሰዎች በኃጢ ያት ከፍያ አማካኝነት ፍጥረታዊ ሰውነ ታቸውን መለወጥ እናም ቅዱሳን ለመሆን ይችላሉ—የኃጢአተኞች ስቃይ እንደባህር እሳትና ዲን ይሆናል። ፲፰፻፴ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንደገና ወንድሞቼ፤ ለእና ንተ የምናገረው ከዚህ በላይ በመጠኑ ስላ ለኝ ትኩረታችሁንም እፈልጋለሁ፤ እነሆ የሚመጣውን በተመለከተ የምነግራችሁ ነገሮች አሉኝና።

፪ እናም የምናገራችሁ ነገሮች በእግዚአብ ሔር [ሁ]መልአክ ተገልፀውልኛል። እርሱም እንዲህ አለኝ፥ ንቃ፤ እናም ነቃሁ፤ እነሆ እርሱም ከፊቴ ቆመ።

፴፤ ሀ ሞዛያ ፫ ፡ ፲፪፤ ሔለ. ፰ ፡ ፳፬–፳፭። ቅ.መ.መ. አመጽ።
ለ አልማ ፮ ፡ ፳፩።
፴፭ ሀ ቅ.መ.መ. መጻጸት፣ ንስሀ መግባት።
ለ ቅ.መ.መ. ፍትህ።
ሐ ቅ.መ.መ. በደል።
፴፱ ሀ አልማ ፴፪ ፡ ፳–፴፣ ፲፭–፲፯። ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።
፴ ሀ አልማ ፭ ፡ ፲፰።
፴፭ ሀ ፬ ኔፊ ፩ ፡ ፲፭–፲፰። ቅ.መ.መ. ደስታ።
ለ ቅ.መ.መ. መባረክ፣ የተባረከ፣ በረከት።
ሐ ት.እና ቃ. ፮ ፡ ፲፫። መ ቅ.መ.መ. ሰማይ።
፫ ፪ ሀ ቅ.መ.መ. መላእክት።

፫ እናም እርሱ እንዲህ አለኝ፥ ንቃ፣
የምነግርህን ቃላት ስማ፤ እነሆም የታላቁን
ደስታ [ሀ]የምስራች ላበስርልህ መጥቻለሁና።
፬ ጌታ ፀሎትህን ሰምቷልና፣ እናም
ፅድቅህንም በሚመለከት ፈርዷልና፤ እናም
አንተ ትደሰት ዘንድና፤ ለህዝብህ ትናገር
ዘንድ፤ እነርሱም ደግሞ በደስታ ይሞሉ
ዘንድ ልኮኛል።
፭ እነሆም፣ በኃይል ሁሉንም የሚገዛው
[ሀ]ጌታ የነገሰው፣ የነበረው፣ እናም ከዘለዓ
ለም እስከ ዘለዓለም ሁሉ የሚኖረው፣ ከሰ
ማይ በሰው ልጆች መካከል የሚመጣበት
ጊዜ ይመጣል፣ ሩቅም አይደለም፣ [ለ]በጭቃ
ሰውነቱ ይኖራልም፤ እናም በሰዎች መካ
ከል፣ በሽተኞችን የመፈወስ፣ ሙታንን
የማስነሳት፣ ሽባዎችን እንዲራመዱ የማ
ድረግ፣ እውሮች ማየት እንዲችሉ፣ ደንቆ
ሮዎችም እንዲሰሙ፣ እናም ሁሉንም የበ
ሽታ ዓይነቶችን ለማዳን [ሐ]አስደናቂ ስራዎ
ችን እየሰራ ይሄዳል።
፮ እናም እርሱ [ሀ]ዲያብሎስን፣ ወይንም
በሰው ልጆች ልብ ውስጥ የሚኖረውን እር
ኩስ መንፈስ ያስወጣል።
፯ እናም እነሆ፣ [ሀ]በፈተናና በስጋዊ
ህመም፣ [ለ]በርሃብ፣ በጥማትና፣ በድካም፤
ከሞት በስተቀር ሰው [ሐ]ሊሰቃይበት ከሚ
ችለው የበለጠም ይሰቃያል፤ እነሆም ለህ
ዝቡ ክፋትና እርኩሰት [መ]ጭንቀቱ እጅግ
ታላቅ ሆኖ፣ [ሠ]ደሙም ከእያንዳንዱ የሰው
ነቱ ቀዳዳ ይፈሳል።
፰ እናም እርሱም [ሀ]ኢየሱስ ክርስቶስ፣
[ለ]የእግዚአብሔር ልጅ፣ የሰማይና የምድር
[ሐ]አባት፣ ከመጀመሪያው ጀምሮ የሁሉም
ነገር ፈጣሪ የነበረ ተብሎ ይጠራል፤ እናም
[መ]እናቱ [ሠ]ማርያም ተብላ ትጠራለች።
፱ እናም እነሆ፣ በስሙ [ሀ]በማመን [ለ]ደህን
ነት ለሰው ልጆች ይመጣ ዘንድ የእርሱ ወደ
ሆኑት መጣ፤ እናም ከዚህ ሁሉ በኋላ እን
ኳን እንደ ሰው ይቆጥሩታል፣ [ሐ]ዲያብሎስ
አለው ብለው ይናገራሉም፤ [መ]ይገርፉታ
ልም፣ እንዲሁም [ሠ]ይሰቅሉታል።
፲ እርሱም [ሀ]በሶስተኛው ቀን [ለ]ከሞት ይነ
ሳል፤ እናም እነሆ ዓለምን [ሐ]ሊፈርድ ይቆ
ማል፤ እናም እነሆ በሰው ልጆች ላይ ጻድ
ቃዊው ፍርድ ይመጣ ዘንድ እነዚህ ሁሉ
ይሆናሉ።
፲፩ እነሆም፣ እናም ደግሞ በአዳም መተ
ላለፍ [ሀ]ለወደቁት ኃጢአተኞች፣ እነርሱን
በተመለከተ ያለውን የእግዚአብሔር ፈቃድ
ሳያውቁ ለሞቱት፣ ወይም [ለ]ባለማወቅ ኃጢ
ያትን ለፈፀሙት የእርሱ [ሐ]ደም [መ]የኃጥያ
ቶች ክፍያ ይሆናል።
፲፪ ነገር ግን በእግዚአብሔር ላይ [ሀ]ማመፁን
ለሚያውቅ ወዮ ወዮለት! እንደነዚያ ላሉት
ደህንነት በንስሃ እና [ለ]በጌታ በኢየሱስ ክር
ስቶስ እምነት ካልሆነ በቀር አይመጣምና።
፲፫ እናም ጌታ እግዚአብሔር ለሁሉም
ወገን፣ ሀገርና፣ ቋንቋ፣ እነዚህን ነገሮች
እንዲናገሩ ቅዱሳን ነቢያቱን በሰው ልጆች
ሁሉ መካከል ልኳል፤ በዚህም ማንኛውም

፫ ሀ ሉቃ. ፪፥፲–፲፩።
፭ ሀ ቅ.መ.መ. ያህዌህ።
ለ ሞዛያ ፯፥፳፯፤
አልማ ፯፥፱–፲፫።
ሐ ማቴ. ፬፥፳፫–፳፬፤
የሐዋ. ፪፥፳፪፤
፩ ኔፊ ፲፩፥፴፩።
ቅ.መ.መ. ተአምራት።
፮ ሀ ማር. ፩፥፴፪–፴፬።
፯ ሀ ቅ.መ.መ. መፈተን፣ ፈተና።
ለ ማቴ. ፬፥፩–፪።
ሐ ት. እና ቃ. ፲፱፥፲፭–፲፰።
መ ኢሳ. ፶፫፥፬–፭።
ሠ ሉቃ. ፳፪፥፵፬።
፰ ሀ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣
አምላክ—እግዚአብሔር
ወልድ።
ለ አልማ ፯፥፲።
ሐ ሔለ. ፲፬፥፲፪፤
፫ ኔፊ ፱፥፲፭።
መ ማቴ. ፩፥፲፮፤
፩ ኔፊ ፲፩፥፲፬–፳፩።
ሠ ቅ.መ.መ. ማርያም፣ የኢየሱስ
እናት።
፱ ሀ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
ለ ቅ.መ.መ. ደህንነት።
ሐ ዮሐ. ፰፥፵፰።
መ ማር. ፲፭፥፲፭።
ሠ ሉቃ. ፲፰፥፴፫፤
፩ ኔፊ ፲፱፥፲፤
፪ ኔፊ ፲፥፫።
ቅ.መ.መ. መስቀል።
፲ ሀ ማቴ. ፲፮፥፳፩፤
፪ ኔፊ ፳፭፥፲፫፤
ሔለ. ፲፬፥፳–፳፯።
ለ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
ሐ ቅ.መ.መ. ዳኛ፣ ፍርድ።
፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. የአዳም እና
የሔዋን ውድቀት።
ለ ፪ ኔፊ ፱፥፳፭–፳፮።
ሐ ቅ.መ.መ. ደም።
መ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ዋጋን
መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ።
፲፪ ሀ ሞዛያ ፪፥፴፮–፴፰፤
ሔለ. ፰፥፳፭።
ቅ.መ.መ. አመጽ።
ለ ቅ.መ.መ. ጌታ።

ክርስቶስ ይመጣል በማለት የሚያምን ለኃጢአቱ [ሀ]ስርየትን ያገኛል፣ እርሱም በመካከላቸውም [ለ]እንደመጣም ዓይነት በታላቅ ደስታ ሃሴት ይሆናሉ።

፲፬ ይሁን እንጂ ጌታ እግዚአብሔር ሕዝቡ አንገተ ደንዳና እንደሆኑ ተመልክቷል፣ እናም ህግን፣ እንዲሁም የሙሴንም [ሀ]ሕግ መስርቶላቸዋል።

፲፭ እናም የእርሱን መምጣት በተመለከተ ብዙ ምልክቶችንና፣ ተዓምራትንና፣ [ሀ]ምሳሌዎችንና ጥላውን አሳይቷቸዋል፤ እናም ደግሞ መምጣቱን በተመለከተ ቅዱሳን ነቢያትም ነግረዋቸዋል፤ ይሁን እንጂ እነርሱ ልባቸውን አጠጥረዋል፣ በደሙ ክፍያም ካልሆነ በቀር የሙሴ [ለ]ሕግ ምንም የማይጠቅም መሆኑን አልተገነዘቡትም።

፲፮ እናም ምንም እንኳን [ሀ]ህጻናት ኃጢያትን መስራት የሚችሉ ቢሆኑም ሊድኑ አይችሉም ነበር፤ ነገር ግን እነርሱ [ለ]የተባረኩ ናቸው እላችኋለሁ፤ እነሆም፣ በአዳም፣ ወይም በፍጥረት እንደወደቁም፣ የክርስቶስ ደም ለኃጢአታቸው ክፍያ እንዲሁም ያደርጋል።

፲፯ እናም ከዚህ በተጨማሪ፣ እንዲህ እላችኋለሁ፣ ሁሉን በሚችለው ጌታ [ሀ]በክርስቶስ ስም ካልሆነ በስተቀር ለሰው ልጆች [ለ]ደህንነት እንዲመጣ የሚሰጥ [ሐ]ምንም ስም ወይም መንገድ፣ ወይም ዘዴ የለም።

፲፰ እነሆም እርሱ ይፈርዳል፣ ፍርዱም ፍፁም ነው፤ እናም በህፃንነቱ የሞተ ህፃን አይጠፋም፤ ነገር ግን ሰዎች እራሳቸውን ትሁትና፣ እንደ ህፃናት [ሀ]ካላደረጉ፣ እናም ሁሉን በሚችለው ጌታ በክርስቶስ የደም [ለ]ካሣ ውስጥና በኩል ደህንነት እንደነበረ፣ እንደሚሆንና፣ እንደሚመጣ ካላመኑ በቀር ኩነኔን ይጎነጫሉ።

፲፱ [ሀ]ተፈጥሮአዊው ሰው ከአዳም [ለ]ውድቀት ጀምሮ ለእግዚአብሔር ጠላት ነው፣ እናም እርሱም [ሐ]ለመንፈስ ቅዱስ ግብዣ [መ]ፈቃደኛ ካልሆነና፣ ተፈጥሮአዊው ሰው ነቱን ካልቀየረ እናም በጌታ በክርስቶስ የኃጢያት ክፍያ አማካኝነት [ሠ]ቅዱስ ካልሆነና፣ [ረ]እንደልጅ ሁሉን የሚቀበል፣ የዋህ፣ ትሁት፣ ትዕግስተኛ፣ በፍቅር የተሞላ፣ ልጅ ከአባቱ ተቀባይ እንደሚሆን፣ ጌታ ብቁ ነው ብሎ የሚያደርስበትን ሁሉንም ነገሮች ለመቀበል ፈቃደኛ ካልሆነ እስከመጨረሻው ለዘለዓለም የእግዚአብሔር ጠላት ይሆናል።

፳ እናም ከዚህ በተጨማሪ፣ እላችኋለሁ፣ የአዳኛችን [ሀ]እውቀት በሁሉም [ለ]ሀገር፣ ነገድ፣ ቋንቋ እና ህዝብ መካከል የሚሰራጭበት ጊዜ ይመጣል።

፳፩ እናም እነሆ፣ ያ ጊዜ ሲመጣ፣ ሁሉን በሚችለው በጌታ እግዚአብሔር ስም ንስሃ እና እምነት በኩል፣ ትናንሽ ልጆች ካልሆኑ በቀር፣ በእግዚአብሔር ፊት [ሀ]እንከን የሌለበት አይገኝም።

፳፪ እናም በዚህ ጊዜም እንኳን ቢሆን፣ ጌታ አምላክህ ያዘዘህን ነገሮች ለሕዝባችሁ ስታስተምር፣ እኔ በነገርኩህ ቃላት መሰረት ካልሆነ በስተቀር ከእንግዲህ በእግዚአብሔር ፊት ያለ እንከን አይሆኑም።

፳፫ እናም አሁን ጌታ እግዚአብሔር ያዘዘኝን ቃላት ተናግሬአለሁ።

፳፬ እናም ጌታ እንዲህ ይላል፥ እነዚህ

፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ስርየት።
ለ ፪ ኔፊ ፳፭፥ ፳፬–፳፯፤ ጀሮም ፩፥ ፲፩።
፲፬ ሀ ቅ.መ.መ. የሙሴ ህግ።
፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—የክርስቶስ ምሳሌዎች እና ምልክቶች።
ለ ሞዛያ ፲፫፥ ፳፯–፴፪።
፲፮ ሀ ቅ.መ.መ. ልጅ፣ ልጆች።
ለ ሞሮኒ ፰፥ ፰–፱።
፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—የክርስቶስን ስም በራሳችን ላይ መውሰድ።
ለ ቅ.መ.መ. ደህንነት።
ሐ የሐዋ. ፬፥ ፲–፲፪፤ ፪ ኔፊ ፴፩፥ ፳፩።
፲፰ ሀ ማቴ. ፲፰፥ ፫።
ለ ሞዛያ ፬፥ ፪፤ ሔለ. ፭፥ ፱።
፲፱ ሀ ፩ ቆሮ. ፪፥ ፲፩–፲፬፤ ሞዛያ ፲፮፥ ፪–፫። ቅ.መ.መ. ፍጥረታዊ ሰው።
ለ ቅ.መ.መ. የአዳም እና የሔዋን ውድቀት።
ሐ ሞሮኒ ፲፥ ፬–፭። ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
መ ፪ ዜና ፴፥ ፰።
ሠ ቅ.መ.መ. ቅዱሳን።
ረ ፫ ኔፊ ፱፥ ፳፪።
፳ ሀ ት. እና ቃ. ፫፥ ፲፮።
ለ ቅ.መ.መ. የሚስዮን ስራ።
፳፩ ሀ ቅ.መ.መ. መልስ መስጠት፣ ሂሳብ፣ ተጠያቂነት፣ ሀላፊነት።

በፍርድ ቀን ለዚህ ሕዝብ እንደ ብሩህ ምስ
ክር ሆነው ይቆማሉ፤ ስለዚህ ማንኛውም
ሰው በስራው መሰረት፣ መጥፎም ሆነ መል
ካም፣ ይፈረድበታል።

፳፭ እናም እነርሱ ደግመው ሊመለሱበት
በማይችሉበት [ሀ]በስቃይና መጨረሻ በሌለው
አሰቃቂ በሆነ ሁኔታ በጌታ ፊት እንዲሸማ
ቀቁ በሚያደርጋቸው በራሳቸው ክፋትና
እርኩሰት ክፉዎች [ለ]አስተያየት ላይ ይመ
ደባሉ፤ ስለዚህ ለእራሳቸው ነፍስ ኩነኔን
ይጎነጫሉ።

፳፮ ስለዚህ፣ ፍርዱ [ሐ]አዳም የተከለከለ
ውን [መ]ፍሬ በመመገቡ መውደቅ እንዳለበት
ለመካድ እንደማይችል እነርሱንም ሊክድ
ስለማይችሉ፣ ከእግዚአብሔር የቁጣ ዋንጫ
ጎንጭተዋል፤ ስለዚህ [ሠ]ምህረት ከእንግ
ዲህ ለዘለዓለም በእነርሱ ላይ ጥያቄ ሊኖ
ረው አይችልም።

፳፯ እናም [ረ]ስቃያቸው ነበልባሉ የማይ
ጠፋ፣ እና ጢሱ ለዘለዓለም እስከ ዘለዓለም
ወደ ላይ እንደሚያርገው እንደ እሳቱ [ሰ]ባህ
ርና ዲን ነው። እንደዚህም ጌታ እኔን አዞ
ኛል። አሜን።

ምዕራፍ ፴

*ንጉስ ቢንያም ንግግሩን ቀጠለ—ደህን
ነት የሚመጣው በኃጢያት ክፍያው አማ
ካኝነት ነው—ለመዳን በእግዚአብሔር
እመኑ—የኃጢአታችሁን ስርየት በእም
ነታችሁ አግኙ—ያላችሁን ነገር ለድሆች
አካፍሉ—ሁሉንም ነገር በጥበብና በስር
ዓት አድርጉ። ፻፳፬ ም.ዓ. ገደማ።*

፩ እናም አሁን፣ እንዲህ ሆነ ንጉስ ቢን
ያም በጌታ መልአክ የተሰጠውን ቃላት ተና
ግሮ ሲጨርስ፣ ዙሪያ ገባውን ተመልክቶ
ዐይኑን በህዝቡ ላይ አሳረፈ፣ እናም የጌታ
[ሀ]ፍርሃት በእነርሱ ላይ በመምጣቱ የተነሳ
በመሬት ላይ ወድቀው ተመለከታቸው።

፪ እናም [ለ]በስጋቸው እራሳቸውን ከመ
ሬት ትቢያ እንኳን [ሐ]አሳንሰው ተመለከቱ።
እናም ሁሉም በአንድ ድምፅ እንዲህ ብለው
ጮሁ፥ አቤቱ ምህረትን ስጠን፣ እናም ለኃ
ጢአታችን ይቅርታን እናገኝ ዘንድና ልባ
ችን ንፁህ ይሆን ዘንድ የክርስቶስን የደም
[መ]ክፍያ በእኛ ላይ አድርግ፤ ሰማይና ምድ
ርን እንዲሁም ሁሉንም ነገሮች [ሠ]በፈጠረው
በሰው ልጆች መካከል በሚመጣው በእግ
ዚአብሔር ልጅ በክርስቶስ ኢየሱስ እና
ምናለንና።

፫ እናም እንዲህ ሆነ እነዚህን ቃላት ከተ
ናገሩ በኋላ የጌታ መንፈስ በእነርሱ ላይ
መጣ፤ እና ንጉስ ቢንያም በተናገረው
ቃላት መሰረት በሚመጣው በኢየሱስ ክር
ስቶስ ባላቸው ታላቅ [ረ]እምነት የተነሳ፣ ለኃ
ጢአታቸውም [ሰ]ስርየትን በመቀበል፣ እናም
[ሸ]የህሊና ሰላምም በማግኘት በደስታ ተሞ
ልተው ነበር።

፬ እናም ንጉስ ቢንያም በድጋሚ አፉን
ከፍቶ እንዲህ ሲል መናገር ጀመረ፥ ጓደ
ኞቼና ወንድሞቼ፣ ወገኖቼና ህዝቤ ለእ
ናንተ የምናገረውን ቀሪውን ቃሌን ታደ
ምጡኝ እናም ትረዱኝ ዘንድ በድጋሚ
ትኩረታችሁን እፈልጋለሁ።

፭ እነሆም በዚህ ጊዜ [ሀ]የእግዚአብሔርን
ቸርነት ማወቅ እናንተ ምንም እንዳልሆና
ችሁ፣ እናም እንደማትረቡና እንደውድቀ
ታችሁ ሁኔታ ስሜት የሚያነቃችሁ ከሆነ—

፮ እንዲህ እላችኋለሁ፣ የእግዚአብሔርን
ቸርነት እናም ወደር የሌለውን ሀይሉንና፣
ጥበቡን፣ እንዲሁም ረዥም ፅናትና፣ እናም
ለሰው ልጆች ያለውን ታጋሽነቱን፣ ደግ

፳፭ *ሀ* ሞር. ፰፡ ፴፰።
ለ አልማ ፭፡ ፲፰፣ ፲፪፡ ፲፡–፲፭።
፳፮ *ሀ* ሞር. ፱፡ ፲፪።
ለ ዘፍጥ. ፫፡ ፭–፲፪፣
፪ ኔፊ ፪፡ ፲፭–፲፱፣
አልማ ፲፪፡ ፳፭–፳፫።
ሐ ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።
፳፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. በደል።
ለ ፪ ኔፊ ፱፡ ፲፮፣
ያዕቆ. ፮፡ ፲፣
ት. እና ቃ. ፫፮፡ ፴፮።
፴ ፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. ፍርሀት።
፪ *ሀ* ቅ.መ.መ. ስጋዊ።
ለ ሔለ. ፲፪፡ ፯–፳።
ሐ ሞዛያ ፫፡ ፲፳፣
ሔለ. ፭፡ ፱።
መ ቅ.መ.መ. መፍጠር፣
ፍጥረት።
፫ *ሀ* ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
ለ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ስርየት።
ሐ ቅ.መ.መ. ህሊና።
፭ *ሀ* ሙሴ ፭፡ ፲።

ሞም ᵐእምነቱን በጌታ ላይ ያሳረፈና፣ ትዕ
ዛዛቱን ለመጠበቅ ትጉህ ለሆነው፣ እና እስ
ከህይወቱ፣ ይህም ማለቴ የስጋ ሰውነት ህይ
ወቱ መጨረሻ ድረስ በእምነት ለጸናው ደህ
ንነት እንዲመጣለት ዘንድ፣ ᵃከዓለም መፈ
ጠር ጀምሮ የተዘጋጀውን ᵇየኃጢያት ክፍያ
ᶜወደማወቅ ከመጣችሁ—

Ꮳ ይህ አይነቱ ሰው ከዓለም መፈጠር
ጀምሮ፣ ከአዳም ᵈውድቀት በኋላ ለነበሩት፣
ወይም ለአሉት፣ ወይም እስከ አለም መጨ
ረሻ ድረስ ስለሚኖሩት፣ ለሰው ልጆች ሁሉ
በተዘጋጀው የኃጢያት ክፍያ ደህንነትን
ይቀበላል እላለሁ።

Ꮵ እናም ደህንነት የሚገኝበት መንገድ
ይህ ነው። እናም ከዚህ ከተነገረው በስተ
ቀር ሌላ ደህንነት ᵉየለም፤ እኔ ከተናገርኳ
ችሁ ሁኔታ በቀር ሰዎች የሚድኑበት ሌላ
መንገድ የለም።

Ꮹ በእግዚአብሔር እመኑ፤ እርሱ እንዳለ፣
እናም እርሱ በሰማይም በምድርም ያሉትን
ሁሉንም ነገሮች እንደፈጠረ እመኑ፤ በሰማ
ይና በምድር ሁሉ ᵐጥበብና ሀይል እንዳለው
እመኑ፤ ጌታ ሊረዳቸው የሚችለውን ነገ
ሮች ሁሉ ሰው ᵃእንደማይረዳቸው እመኑ።

Ꮺ እናም እንደገና፤ ለኃጢአታችሁ ᵐንስሃ
መግባትና፣ መተው፣ እንዲሁም በእግዚ
አብሔር ፊት ትሁት መሆን እንዳለባችሁ
እመኑ፤ ᵃይቅር እንድትባሉ ከልባችሁም
ጠይቁ፤ እናም አሁን፣ እነዚህን ነገሮች
ሁሉ ᵐካመናችሁ ᵐመፈፀማችሁን አረጋ
ግጡ።

ᏬᏩ እናም እንደገና በፊት እንደተናገር
ኳችሁ እናገራችኋለሁ፣ የእግዚአብሔርን
ክብር ለማወቅ የምትመጡ ከሆነ፣ እንዲ
ሁም ቸርነቱንና ታጋሽነቱን ካወቃችሁና
ፍቅሩን ᵐከቀመሳችሁ፣ ነፍሳችሁ እጅግ
እንድትደሰት የሚያደርገውን ለኃጢአታ
ችሁ ᵃስርየትን ከተቀበላችሁም፣ የእግዚአ
ብሔርን ታላቅነትና የራሳችሁን ᵐከንቱነት፣
ወደ እናንተ የማትረቡ ፍጥረት ያለውን የእ
ርሱን ᵐጥሩነትና ትዕግስት፣ እናም የጌታ
ንም ስም ቀን በቀን ᵐበመጥራትና በመል
አኩ አፍ በተነገረለት ወደፊት በሚመጣው
እምነት አፅንታችሁ በመቆም በጥልቅ ᶜትህ
ትና እንኳን ራሳችሁን እንድታዋርዱ እን
ድታስታውሱትና ሁልጊዜም በማስታወስ
እንድትይዙት እፈልጋለሁ።

ᏬᏫ እናም እነሆ፣ እላችኋለሁ ይህንን የም
ታደርጉ ከሆነ ሁልጊዜ ትደሰታላችሁ፣ በእ
ግዚአብሔር ᵐፍቅር ትሞላላችሁም፣ ሁል
ጊዜ የኃጢአታችሁን ስርየት ᵃታገኛላች
ሁም፤ እናም እናንተን በፈጠረው ክብር
እውቀት፣ ወይንም ትክክለኛና እውነተኛ
በሆነው እውቀት ታድጋላችሁ።

ᏬᏮ እናም ᵐበሰላም ለመኖርና፣ ለእያን
ዳንዱ ሰው የሚገባውን ለመስጠት እንጂ፣
እርስ በርሳችሁ የመጎዳዳት ሃሳብ አይኖር
ባችሁም።

ᏬᏯ እናም ᵐልጆቻችሁ ተርበው አለበለዚ
ያም ተራቁተው እንዲሄዱ አትፈቅዱም፤
የእግዚአብሔርንም ህግ እንዲተላለፉ፣
እርስ በርሳቸውም ᵃእንዲጣሉ እናም በአ
ባቶቻችን ክፉ መንፈስ ተብሎ የተነገረለ
ትን የፅድቅ ሁሉ ጠላት የሆነውንና የኃጢ

ᏣᏥ *ሀ* መዝ. ᏭᏦ፡ ᏣᏥ፤
ᏪᏬ ᏄᏬ ᏣᏪ፡ ᏪᏬ፤
ሌሊ. ᏬᏪ፡ ᏩᏬ።
ቅ.መ.መ. መታመን።
ለ ሞዛያ ᏬᏣ፡ ᏬᏪᏪ።
ሐ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ዋጋን
መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ።
መ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣
አምላክ።
ᏣᏥ *ሀ* ቅ.መ.መ. የአዳም እና
የሔዋን ውድቀት።
ᏣᏫ *ሀ* የሐዋ. ᏚᏬ፡ ᏬᏪᏪ፤
ᏪᏬ ᏄᏬᏩ፡ ᏣᏩᏩ፤
ሞዛያ ᏫᏬ፡ ᏬᏦᏪ።
ᏪᏬ *ሀ* ሮሜ ᏬᏩ፡ ᏭᏫᏫ–ᏭᏪᏪ፤
ያዕቆ. ᏚᏬ፡ ᏣᏬ–ᏬᏫᏫ።
ለ ኢሳ. ᏪᏣᏩ፡ ᏪᏬ።
ᏬᏬ *ሀ* ቅ.መ.መ. መጸጸት፣ ንስሀ
መግባት።
ለ ት. እና ቃ. ᏣᏩᏩ፡ ᏪᏬ።
ሐ ማቴ. ᏦᏬ፡ ᏣᏣᏪ–ᏣᏣᏦ።
መ ᏪᏬ ᏄᏬ ᏭᏩᏩ፡ ᏬᏪ–ᏣᏩᏩ።
ᏬᏩᏩ *ሀ* አልማ ᏭᏦᏦ፡ ᏣᏪᏪ–ᏣᏣᏦ።
ለ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ስርየት።
ሐ ሙሴ ᏩᏬ፡ ᏬᏬ።
መ ዘፀአ. ᏭᏪᏪ፡ ᏦᏬ፤
ሞሮኒ ᏣᏬ፡ ᏫᏬ።
ሠ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
ረ ቅ.መ.መ. ትሁት፣ ትሕትና።
ᏬᏪᏪ *ሀ* ቅ.መ.መ. ፍቅር።
ለ ሞዛያ ᏪᏬ፡ ᏣᏣᏦ፤
አልማ ᏪᏬ፡ ᏬᏫᏫ–ᏬᏪᏪ፤ ᏩᏬ፡ ᏣᏣᏦ–
ᏭᏪᏩ፤
ት. እና ቃ. ᏣᏬ፡ ᏭᏩᏩ–ᏭᏪᏪ።
ᏬᏫᏫ *ሀ* ቅ.መ.መ. ሰላም የሚሰራ።
ᏬᏪᏪ *ሀ* ᏩᏬ ጢሞ. ᏩᏬ፡ ᏣᏬ፤
ት. እና ቃ. ᏭᏫᏫ፡ ᏪᏬ።
ለ ቅ.መ.መ. ጸብ።

ያት አለቃ የሆነውን ዲያብሎስን እንዲያገ
ለግሉ አትፈቅዱም።
፲፭ ነገር ግን በእውነትና በጥሞና መንገድ
[ሀ]እንዲራመዱ [ለ]ታስተምሯቸዋላችሁ፣
እርስ በርሳቸው [ሐ]እንዲዋደዱ እንዲሁም
አንደኛው ሌላኛውን እንዲያገለግል ታስ
ተምሯቸዋላችሁ።
፲፮ እናም ደግሞ፣ እናንተ ራሳችሁ የእ
ናንተን [ሀ]እርዳታ ፍለጋ የቆሙትን ትረዷ
ቸዋላችሁ፤ ፍላጎት ላላቸው ቁሳቁሳችሁን
ትሰጧቸዋላችሁ፤ እናም [ለ]ለማኙም እናን
ተን የሚለምነው በከንቱ እንዲሆንና፣ እን
ዲጠፋ ማስወጣትን አትፈቅዱም።
፲፯ ምናልባት እንዲህ [ሀ]ትላላችሁ፥ ይህ
ሰው ስቃይን በራሱ ላይ አምጥቷል፣ ስለሆ
ነም እጄን እሰበስባለሁ፣ እናም እንዳይቸገር
ከእንጀራዬም ሆነ ከአለኝ ነገር አልሰጠውም
ምክንያቱም ቅጣቶቹ ትክክል ናቸውና—
፲፰ ነገር ግን እላችኋለሁ፣ ሰው ሆይ፣
ማንም ይህንን ያደረገ ንስሃ ለመግባት
ታላቅ ምክንያት ይኖረዋል፤ እናም በፈ
ፀመው ነገር ንስሃ ካልገባ በስተቀር ለዘለዓ
ለም ይጠፋል፣ እናም በእግዚአብሔር መን
ግስት ቦታ አይኖረውም።
፲፱ እነሆም ሁላችንስ ለማኞች አይደለ
ንምን? ሁላችንም ባሉን ቁሳቁሶች ሁሉ፣
በምግብና በልብስ፣ እንዲሁም በወርቅና፣
በብር፣ እናም ከሁሉም አይነት ባሉን ሀብ
ቶች በአንዱስ ፍጡር፣ እንዲሁም በእግዚ
አብሔር ጥገኞች አይደለንምን?
፳ እናም እነሆ፣ በዚህ ጊዜም እንኳን
ቢሆን፣ ስሙን ጠርታችኋልም፣ ለኃጢ
አታችሁ ስርየትን ለምናችኋልም። እናም
በከንቱ እንድትለምኑ ፈቅዷልን? አይደ
ለም፤ መንፈሱን በላያችሁ ላይ አፍስሷል፤
እናም ልባችሁ [ሀ]በደስታ እንዲሞላ አድ
ርጓል፣ እንዲሁም ስለዚህ ደስታችሁም
እጅግ ታላቅ ሆኖ፣ መናገርም እንዳትችሉ
አንደበታችሁን እንዲዘጋ አድርጓል።
፳፩ እናም አሁን፣ ለህይወታችሁና ላላች
ሁና ለሆናችሁት ሁሉ የምትመኩበት እና
ንተን የፈጠረው እግዚአብሔር ትክክለኛ
የሆነውን ማንኛውንም ነገር በእምነት፣ አገ
ኛለሁ በማለት አምናችሁ የምትጠይቁትን
ከሰጣችሁ፣ አቤቱ ያላችሁን ነገሮች አንዳ
ችሁ ለሌላኛችሁ እንዴት [ሀ]መካፈል ይገ
ባችኋል።
፳፪ እናም አንድ ሰው እንዳይጠፋ ካላ
ችሁ ሀብት እንድታካፍሉት የሚጠይቃች
ሁን [ሀ]ከፈረዳችሁበት፣ ከኮነናችሁት፣ የእ
ናንተ ሳይሆን ህይወታችሁም እንኳን የእ
ርሱ የሆነው የእግዚአብሔር የሆነውን ሀብ
ታችሁን [ለ]በመያዛችሁ ኩነኔያችሁም ምን
ያህል ትክክል ይሆናል፤ ነገር ግን፣ ለሰራ
ችኋቸው ነገሮችም ንስሃን እናም ልመናን
አላቀረባችሁም።
፳፫ እላችኋለሁ፣ ለዚህ ሰው ወዮለት
ያለው ነገር ከእርሱ ጋር ይጠፋልና፣ እናም
አሁን፣ የዚህን ዓለም ነገሮች ለአሉአቸው
[ሀ]ባለጠጋዎች እነዚህን ነገሮች እናገራለሁ።
፳፬ እናም እንደገና ባይኖራቸውም፣ ግን
በህይወት እንዲቆዩ በመጠኑም ለሚኖራ
ቸው ድሆች እንደገና እንዲህ እላለሁ፤
ማለቴም እናንተ ስለሌላችሁ ለድሆች ለማ
ትሰጡት ነው፤ በልባችሁ ስለሌለኝ አይደ
ለም የማልሰጠው፣ ነገር ግን ቢኖረኝ ኖሮ
[ሀ]እሰጥ ነበር እንድትሉ እፈልጋለሁ።
፳፭ እናም አሁን፣ ይህንን በልባችሁ የም
ትሉ ከሆነ ከበደል የነፃችሁ ትሆናላችሁ፣
አለበለዚያ ግን [ሀ]ትኮነናላችሁ፣ እናም ኩነኔ
አችሁ የእናንተ ያልሆነውን በመመኘታችሁ
ትክክል ነው።

፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. መራመድ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መራመድ (መሄድ)።
ለ ት. እና ቃ. ፳፰፥፳፭–፳፰፤ ሙሴ ፮፥፶፰።
ቅ.መ.መ. ማስተማር፣ አስተማሪ።
ሐ ሞዛያ ፲፰፥፳፩።
፲፮ ሀ ቅ.መ.መ. ልግስና፤ አገልግሎት።
ለ ዘዳግ. ፲፭፥፯–፲፩፤ ምሳ. ፳፩፥፲፫፤ ኢሳ. ፲፥፩–፪።
፲፯ ሀ ምሳ. ፲፯፥፭።
፳ ሀ ቅ.መ.መ. ደስታ።
፳፩ ሀ ቅ.መ.መ. በጎ ድርገት፤ አገልግሎት።
፳፪ ሀ ማቴ. ፯፥፩–፪፤ ዮሐ. ፯፥፳፬።
ለ ፩ ዮሐ. ፫፥፲፯።
፳፫ ሀ ት. እና ቃ. ፶፮፥፲፮።
፳፬ ሀ ማር. ፲፪፥፵፬።
፳፭ ሀ ት. እና ቃ. ፶፮፥፲፯።

ᏋᏬ እናም አሁን፣ ለእናንተ ለተናገር ኋቸው ለእነዚህ ነገሮች ሲባል—ይህም ማለት በእግዚአብሔር ፊት ከበደል ነፅታ ችሁ ᵐትራመዱ ዘንድ ከቀን ወደ ቀን ለኃ ጢአታችሁ ስርየትን እንድታገኙ—የራ ሳችሁን ነገር ᵃለድሃ ᵐእንድትሰጡ፣ እያ ንዳንዱ ሰው ባለው መጠን፣ የተራቡትን ᵐበመመገብ፣ የታረዙትን በማልበስ፣ የታ መሙትን በመጎብኘት እናም እንደፍላጎታ ቸው ለነፍሳቸውም ሆነ ለስጋቸው ደህንነት በቂ እርዳታን እንድትለግሱ እፈልጋለሁ።

ᏋᏭ እናም እነዚህ ነገሮች ሁሉ በጥበብና በዕቅድ እንደተደረጉ ተመልከቱ፣ ሰው ከአቅሙ በላይ ᵐፈጥኖ መሮጡ አስፈላጊ አይደለምና። እናም እንደገና፣ ሽልማቱን ያሸንፍ ዘንድ ትጉህ መሆኑ አስፈላጊ ነው፣ ስለዚህ፣ ሁሉም ነገሮች በስርዓት መደረግ አለባቸው።

ᏋᏮ እናም ማንም ከእናንተ መካከል ከጎ ረቤቱ የተበደረ የተበደረውን ነገር በስምም ነቱ መሰረት መመለስ እንዳለበት እንድታስ ታውሱ እፈልጋለሁ፣ አለበለዚያ ኃጢያትን ትፈፅማላችሁ፤ እናም ምናልባት ጎረቤቶ ቻችሁንም ደግሞ ኃጢያት እንዲፈፅሙ ታደርጋላችሁ።

ᏋᏯ እናም በመጨረሻም፣ ኃጢያት ልትፈፅሙ የምትችሉባቸውን ነገሮች ሁሉ ልነግራችሁ አልችልም፤ ምክንያቱን መቁ ጠር የማልችለው ብዙ መንገዶችና ዘዴዎች ስለሚኖሩ ነው።

ᏰᏂ ነገር ግን ይህን ያህል ልነግራችሁ እች ላለሁ፣ ራሳችሁን፣ ᵐሀሳባችሁንና፣ ᵃቃላች ሁን፣ እናም ድርጊታችሁን የማታስተው ሉና፣ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ᵐየማትጠ ብቁ፣ እናም የሚመጣውን ጌታችንን በተ መለከተ የሰማችሁትን እስከ ህይወታችሁ መጨረሻ በእምነት የማትቀጥሉ ከሆናችሁ፣ መጥፋት ይገባችኋል። እናም አሁን፣ ሰው ሆይ፣ አስታውስ፣ እናም አትጥፋ።

ምዕራፍ ᏏᏬ

ቅዱሳን በእምነታቸው የክርስቶስ ወን ዶች እና ሴቶች ልጆች ይሆናሉ—ከዚ ያም በክርስቶስ ስም ይጠራሉ—ንጉስ ቢ ንያም በመልካም ስራቸው እንዲፀኑ እናም የማይነቃነቁ እንዲሆኑ መከራቸው። በᎮᏋᏮ ም.ዓ. ገደማ።

ᏏᏭ እናም አሁን፣ እንዲህ ሆነ ንጉስ ቢን ያም ለህዝቡ እንደዚህ በተናገረ ጊዜ፣ ለእነ ርሱ የተናገረውን አምነው እንደሆነ ከህዝቡ ለማወቅ በመፈለጉ በመካከላቸው ሰው ላከ።

ᏏᏯ እናም ሁሉም በአንድ ድምፅ እን ዲህ በማለት ጮኹ፥ አዎን፣ ለእኛ የተ ናገርካቸውን ቃላት በሙሉ እናምናለን፤ እናም ደግሞ ያለማቋረጥ መልካምን መስ ራት እንጂ ከእንግዲህ ᵐኃጢያት ለመፈፀም ምንም ፍላጎት እንዳይኖረን ታላቅ ᵃለውጥ ለእኛ ወይንም በልባችን ውስጥ በሰራው ሁሉን በሚገዛው በጌታ መንፈስ አማካኝ ነት እርግጠኝነታቸውን እና እውነተኛነታ ቸውን አውቀናል።

ᏐᏂ እናም እኛ፣ እራሳችን ደግሞ በማይወ ሰነው የእግዚአብሔር ቸርነትና፣ በመንፈሱ መገለጥ ስለሚመጣው ታላቅ አመለካከት አለን፤ እናም የሚያስፈልግ ቢሆን እንኳን፣ ስለ ሁሉም ነገሮች መተንበይ እንችላለን።

ᏐᏮ እናም እጅግም ታላቅ በሆነ ደስታ ወደ ምንደሰትበት ወደዚህ ታላቅ እውቀት ያመ ጣን፣ የእኛ ንጉስ በተናገራቸው ነገሮች አን ፃር ያለን እምነት ነው።

ᏐᏯ እናም ከእግዚአብሔር ጋር ፈቃዱን

ᏋᏬ *ሀ* ቅ.መ.መ. መራመድ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መራመድ (መሄድ)።
ለ ዘካ. ᏎᏫ፤ ᏐᏫ፤ አልማ ᏏᏬᏋᏬ።
ቅ.መ.መ. ምፅዋት፣ የምፅዋት ስጦታ።
ሐ ያዕቆ. ᏇᏫ–ᏐᏬ–ᏐᏰᏫ።
መ ኢሳ. ᎮᏋᏫ–ᏐᏬᏫ፤ ት. እና ቃ. ᎮᏰᏫ–ᏐᏋᏫ።
ᏋᏬ *ሀ* ት. እና ቃ. ᏐᏫᏇᏫ።
ᏰᏂ *ሀ* ማር. ᏎᏫ–ᏐᏋᏫ–ᏋᏬᏫ።
ቅ.መ.መ. ሀሳቦች።
ለ ማቴ. ᏐᏏᏫ–ᏐᏋᏫ–ᏋᏫ።
ቅ.መ.መ. ማራከስ።
ሐ አልማ ᏐᏇᏫ–ᏐᏰᏫ።
ቅ.መ.መ. መጠበቅ፣ ጠባቂ።
ᏏᏬ ᏇᏂ *ሀ* አልማ ᏐᏰᏫ–ᏰᏬᏫ።
ለ አልማ ᏏᏫ–ᏐᏰᏫ።
ቅ.መ.መ. ዳግመኛ መወለድን፣ ከእግዚአብሔር መወለድ።

ለማድረግ እናም በቀረው ጊዜአችን ሁሉ
እኛን ባዘዘን በሁሉም ነገር ለትዕዛዛቱ ታዛ
ዦች ለመሆን፣ መጨረሻ የሌለው ᵐቅጣት
በራሳችን ላይ እንዳናመጣ፣ ᵃበመልአኩ
እንደተነገረው ከእግዚአብሔር የቁጣ ዋንጫ
እንዳንጎነጭ ከአምላካችን ጋር ᵃቃል ኪዳን
ለመግባት ፈቃደኞች ነን።

፮ እናም አሁን፣ ንጉስ ቢንያም ከእነርሱ
የፈለጋቸው ቃላት እነዚህ ናቸው፤ እናም
ስለዚህ እንዲህ አላቸው፥ እናንተ እኔ የፈ
ለኳቸውን ቃላት ተናግራችኋል፤ እናም
የገባችሁት ቃል ኪዳን የጽድቅ ቃል ኪዳን
ነው።

፯ እናም አሁን፣ በገባችሁት ቃል ኪዳን
የተነሳ የክርስቶስ ᵐልጆች፣ ወንዶችና ሴት
ልጆቹ፣ ተብላችሁ ትጠራላችሁ፤ እነሆም
በዚህ ቀን እናንተን በመንፈስ ᵃወልዷ
ኋል፤ ᵃልባችሁ በስሙ በማመን ተለው
ጧል ብላችኋልና፤ ስለዚህ እናንተ ከእርሱ
ᵐተወልዳችኋል እናም የእርሱ ᵐወንዶችና
ሴቶች ልጆች ሆናችኋል።

፰ እናም በዚህ ራስ ስር ᵐነፃ ተደርጋችኋል
እናም በራሱ ነፃ መሆን የምትችሉበት ᵃሌላ
ምንም የለም። ደህንነት ሊመጣበት የሚ
ችል ሌላ ᵃስም የለም፤ ስለዚህ የክርስቶስን
ስም ᵐእንድትወስዱ እፈልጋለሁ፣ ሁላች
ሁም ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን የገ
ባችሁ እስከህይወታችሁ መጨረሻ ታዛዥ
እንድትሆኑ እመኛለሁ።

፱ እናም እንዲህ ይሆናል፣ ማንም ይህ
ንን ያደረገ በእግዚአብሔር ቀኝ ይገኛል፣
የሚታወቅበትን ስም ያውቃልና፤ በክርስ
ቶስ ስም ይጠራልና።

፲ እናም አሁን እንዲህ ይሆናል፣ የክርስ
ቶስን ስም ያልለበሰ ማንኛውም ᵐበሌላ ስም
መታወቅ አለበት፤ ስለዚህ፣ እራሱን በእግ
ዚአብሔር ᵃግራ በኩል ያገኛል።

፲፩ እናም ይህን ደግሞ እንድታስታውሱ
እፈልጋለሁ፣ በመተላለፍ ካልሆነ በቀር
ለእናንተ መስጠት አለብኝ ያልኩት የማ
ይደመሰሰው ᵐስም ይህ ነው፤ ስለዚህ፣
ስሙም ከልባችሁ እንዳይጠፋ ዘንድ እን
ዳትተላለፉ አስተውሉ።

፲፪ በእግዚአብሔር ግራ እንዳትገኙ፣ ነገር
ግን የምትጠሩበትን ድምፅ፣ እናም ደግሞ
በእርሱ የምትጠሩበትን ስም እንድታዳ
ምጡና እንድታውቁ፣ በልባችሁ የተፃፈ
ውን ስም ሁልጊዜ ᵐእንድትጠብቁ እፈል
ጋለሁ እላችኋለሁ።

፲፫ ያላገለገለውን አለቃ፣ እና ለእርሱ እን
ግዳ የሆነውን፣ ከልቡ ስሜትና ሀሳብ የራ
ቀውን፣ አንድ ሰው እንዴት ᵐያውቃል?

፲፬ እናም ሰው እንደገና የጎረቤቱ የሆነውን
አህያ ወስዶ የእርሱ ያደርገዋልን? አያደር
ግም እላችኋለሁ፣ ከመንጋዎቹ ጋር እንኳን
እንዲመገብ አይፈቅድም፣ ነገር ግን ያስወ
ጣታል እናም ያሳድዳታል። እላችኋለሁ፣
የምትጠሩበትን ስም የማታውቁ ከሆነ በእ
ናንተ መካከል እንኳን እንዲህ ይሆናል።

፲፭ ስለዚህ፣ ሁሉን የሚገዛ ጌታ ክርስ
ቶስ ወደ ሰማይ ትመጡ ዘንድ፣ ከሁሉም
በላይ አምላክ የሆነው በሰማይና በምድር
ያሉትን ነገሮች ሁሉ ᵐበፈጠረ፣ ጥበብ፣
ሀይል፣ እና ፍርድ፣ እንዲሁም በምህረቱ
ዘለዓለማዊ ደህንነትና ዘለዓለማዊ ህይወት
እንዲኖራችሁ የእርሱ እንድትሆኑ ᵃያት

፭ ሀ ሞዛያ ፫፡ ፳፭–፳፯።
ለ ሞዛያ ፫፡ ፪።
ሐ ሞዛያ ፲፰፡ ፲።
፯ ሀ ሞዛያ ፳፯፡ ፳፱–፳፯፤
ሙሴ ፮፡ ፳፱–፴፰።
ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር
ወንድ እና ሴት ልጆች።
ለ ቅ.መ.መ. መወለድ።
ሐ ቅ.መ.መ. ልብ።
መ ሞዛያ ፲፭፡ ፣–፲፩።
ቅ.መ.መ. ዳግመኛ
መወለድን፣ ከእግዚአብሔር
መወለድ።
ሠ ት. እና ቃ. ፲፩፡ ፴።
፴ ሀ ሮሜ ፮፡ ፣፲፡
ገላ. ፭፡ ፩፣
ሔለ. ፲፡ ፴።
ለ የሐዋ. ፡ ፣ ፣ ፲፪፣
አልማ ፳፩፡ ፱።
ሐ ሞዛያ ፳፯፡ ፣፲።
መ የሐዋ. ፣፩፡ ፳፯፣
አልማ ፴፯፡ ፣፲፡
፣ ሀ አልማ ፭፡ ፴፣–፴፱።
ለ ማቴ. ፳፭፡ ፴፣።
፣፩ ሀ ሞዛያ ፩፡ ፣፩–፣፪።
ቅ.መ.መ. ኢየሱስ
ክርስቶስ—የክርስቶስን ስም
በራሳችን ላይ መውሰድ።
፣፪ ሀ ት. እና ቃ. ፣፲፡ ፳፣–፳፭።
፣፣ ሀ ሞዛያ ፳፯፡ ፳፡–፳፯።
፣፭ ሀ ቁላ. ፩፡ ፣፯፣
ሞዛያ ፪፡ ፪፣
አልማ ፣፩፡ ፴፱።
ለ ቅ.መ.መ. መጠራት እና
መመረጥ፣
ቅድስና።

ምላችሁ ዘንድ እናንተ ፅኑ እናም የማትነ ቃነቁ፣ ሁልጊዜም በመልካም ስራ የተሞ ላችሁ እንድትሆኑ እፈልጋለሁ። አሜን።

ምዕራፍ ፮

ንጉስ ቢንያም የህዝቡን ስም መዘገበ እናም እነርሱን የሚያስተምሩ ካህናትን ሾመ—ሞዛያ ፃድቅ ንጉስ በመሆን ነገሰ። ከ፲፯፻፱–፲፯፻፭ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም አሁን፣ ንጉስ ቢንያም ለህዝቡ ንግግሩን ከጨረሰ በኋላ፣ የእግዚአብሔ ርን ትዕዛዛት ለመጠበቅ ቃል ኪዳን የገቡ ትን ሁሉ ስም [a]መመዝገቡ ጠቃሚ እንደ ነበር አሰበ።

፪ እናም እንዲህ ሆነ ከትናንሽ ህፃናት በስ ተቀር፣ ነገር ግን ወደ ቃል ኪዳኑ ያልገባና የክርስቶስን ስም ያልለበሰ አንድም ነፍስ አልነበረም።

፫ እናም እንደገና፣ እንዲህ ሆነ ንጉስ ቢንያም እነዚህን ነገሮች ሁሉ ሲጨርስ፣ እናም ልጁን [b]ሞዛያን በህዝቡ ላይ ገዢና ንጉስ አድርጎ ከቀድሰውና መንግስቱን በተ መለከተ ሁሉንም ሃላፊነት ከሰጠው፣ ደግ ሞም የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ያደምጡና ያውቁ ዘንድ እናም የፈፀሙትን [c]መሀላ እንዲያስተውሉ ለማነሳሳት ካህናት ህዝ ቡን [d]እንዲያስተምሩ [e]ከሾማቸው በኋላ፣ ህዝቡን አሰናበተ፣ እናም ሁሉም ከየቤተ ሰቦቻቸው ጋር ወደየቤታቸው ተመለሱ።

፬ እናም [f]ሞዛያ በአባቱ ቦታ መንገስ ጀመረ። እናም ንግስናውን በሰላሳ አመቱ ጀመረ፣ ይኸውም ሌሂ ኢየሩሳሌምን ለቆ ከወጣ [g]ጊዜ በአጠቃላይ አራት መቶ ሰባ ስድስት አመት ገደማ ይሆናል።

፭ እናም ንጉስ ቢንያም ለሶስት ዓመታት ኖረ፣ እናም ሞተ።

፮ እናም እንዲህ ሆነ ንጉስ ሞዛያ በጌታ መንገድ ተራምዷል፣ የጌታን ፍርድና ስር አት አስተውሏልም፣ እናም በሁሉም ነገ ሮች እርሱ ያዘዘውን ጠብቋል።

፯ እናም ንጉስ ሞዛያ ህዝቡ መሬትን እን ዲያርስ አደረገ። እናም ደግሞ ለህዝቡ [h]ሽክም እንዳይሆን በሁሉም ነገር አባቱ እን ዳደረገው ያደርግ ዘንድ እራሱም መሬትን ያርስ ነበር። እናም ለሶስት ዓመታት ያህል በህዝቡ ሁሉ መካከል ጠብ አልነበረም።

ምዕራፍ ፯

አምን ሊምሂ ንጉሥ የሆነበትን፣ የሌሂ-ኔፊ ምድርን አገኘ—የሊምሂ ህዝብ በላማና ውያን ባርነት ስር ናቸው—ሊምሂ ታሪ ካቸውን ዘገበ—ነቢዩ (አቢናዲ) ክርስቶስ የሁሉም ነገሮች አምላክና አባት መሆኑን መስክሯል—መጥፎ የዘሩ አውሎ ነፋስን ያጭዳሉ፣ እናም በጌታ እምነታቸውን ያደረጉ ይድናሉ። ፲፯፻፭ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም አሁን፣ እንዲህ ሆነ ንጉሥ ሞዛያ ለሦስት ዓመታት ያህል ያለማቋረጥ ሠላ ምን ካገኘ በኋላ፣ በሌሂ-ኔፊ ምድር እንዲ ሁም በሌሂ-ኔፊ ከተማ ለመኖር [i]የሄዱትን ሕዝቦች በተመለከተ ለማወቅ ፈለገ፤ ምክ ንያቱም ህዝቡ [j]የዛራሄምላን ምድር ለቀው ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ ምንም አልሰሙም ነበረ፤ ስለዚህ፣ በጥያቄያቸው ረበሹት።

፪ እናም እንዲህ ሆነ ወደ ሌሂ-ኔፊ ምድር ወንድሞቻቸውን በተመለከተ ይጠይቁ ዘንድ ንጉሥ ቢንያም ከጠንካሮቹ አስራ ስድስቱ እንዲሄዱ አደረገ።

፫ እናም እንዲህ ሆነ በማግስቱ የዛራሔምላ ትውልድ የሆነውንና ጠንካራና ኃይለኛ የሆ ነውን ሰው አሞንን ይዘው መሄድ ጀመሩ፤ እናም ደግሞ እርሱ መሪያቸው ነበር።

፬ እናም አሁን፣ ወደ ሌሂ-ኔፊ ምድር ለመሄድ በምድረበዳ ውስጥ መጓዝ ያለ

፮ [a] ሀ ት.እና ቃ. ፲፯፻፰፡፰።
፫ [b] ሀ ሞዛያ ፩፡፲፡ ፪፡፴።
[c] ለ ሞዛያ ፩፡፩–፯።
[d] ሐ ቅ.መ.መ. መሾም፣ ሹመት።
[e] መ አልማ ፩፡፯።
፬ [f] ሀ ቅ.መ.መ. ሞዛያ፣ የቢንያም ልጅ።
[g] ለ ኔፊ ፩፡፬።
[h] ሀ ፪ ቆሮ. ፲፩፡፱።
[i] ሀ ኦምኒ ፩፡፳፯–፴፡
[j] ለ ኦምኒ ፩፡፲፫።

ባቸውን መንገድ አላወቁትም፤ ስለዚህ፣ በምድረበዳ ውስጥ ለብዙ ቀናት ዞሩ፣ እን ዲህም ለአርባ ቀናት ዞሩ።

፮ እናም አርባ ቀን ከዞሩ በኋላ ᵐከሺሎም ምድር በስተሰሜን ወደነበረ አንድ ኮረብታ መጡና በዚያም ቦታ ድንኳናቸውን ተከሉ።

፯ እናም አሞን ሶስቱን ወንድሞቹን ወሰደ፣ እናም ስማቸውም አማሌቂ፣ ሔለ ምና፣ ሔም ነበር፣ እናም ወደ ᵐኔፊ ምድር ወረዱ።

፰ እናም እነሆ፣ በኔፊ ምድርና፣ በሺሎም ምድር የነበሩትን ሰዎች ንጉሥ ተገናኙት፤ እናም እነርሱ በንጉሡ ጠባቂዎች ተከ በቡና፣ ተወሰዱ፣ እንዲሁም ተያዙና ወደ ወህኒ ተጣሉ።

፱ እናም እንዲህ ሆነ ለሁለት ቀናት በወህኒ በነበሩበት ጊዜ እንደገና በንጉሡ ፊት ቀር በው ነበር፣ እናም እስራታቸውም ተፈትቶ ላቸው ነበር፤ እናም በንጉሱ ፊት ቆሙና፣ እርሱ የሚጠይቃቸውን ጥያቄዎች እንዲ መልሱ ተፈቀደላቸው ወይም ታዘዙ።

፱ እናም እንዲህ አላቸው፥ እነሆ እኔ፣ ከዛራሔምላ ምድር የአባታቸው ምድር የነበረውን ይህንን ምድር ለመውረስ የመ ጣው፣ በህዝብ ድምፅ ንጉሥ የተደረገው የዜኒፍ ልጅ፣ የኖህ ልጅ ᵐሊምሂ ነኝ።

፲ እናም አሁን፣ እኔ ከራሴ ጠባቂዎች ጋር ከግቢው ውጭ በነበርኩበት ጊዜ ወደ ከተ ማው ክልል ለመምጣት የደፈራችሁበትን ምክንያት ለማወቅ እፈልጋለሁ?

፲፩ እናም አሁን፣ እናንተ እንድትጠበቁ ያደረኩበት ምክንያት እናንተን እጠይቅ ዘንድ ነው፣ አለበለዚያ ጠባቂዎቼ እንዲ ገድሉአችሁ አደርግ ነበር። እናንተም እን ድትናገሩ ተፈቅዶላችኋል።

፲፪ እናም አሁን፣ አሞን ለመናገር እንደ ተፈቀደለት በተመለከተ ጊዜ፣ ሄደና በን ጉሱ ፊት ሰገደ፤ እናም እንደገና ተነስቶ እንዲህ አለ፥ ንጉስ ሆይ፣ በዛሬ ቀን በህ ይወት በመኖሬና ለመናገር ስለተፈቀደልኝ በእግዚአብሔር ፊት እጅግ አመሰግናለሁ፤ እናም በድፍረት ለመናገር እሞክራለሁ፤

፲፫ እኔን ብታውቀኝ ኖሮ ይህንን ማሰሪያ እንዳጠልቅ እንደማትፈቅድ እርግጠኛ ነበ ርኩ። እኔ አሞን ነኝ፣ እናም ᵐየዛራሔምላ ዘር ነኝ፣ እናም ዜኒፍ ከምድሪቱ ስላ ወጣቸው ስለወንድሞቻችን ለመጠየቅ ከዛራሔምላ ምድር መጥቻለሁ።

፲፬ እናም አሁን፣ እንዲህ ሆነ ሊምሂ የአ ሞንን ቃላት ከሰማ በኋላ እጅግ ተደሰተ፣ እናም እንዲህ አለ፥ አሁን፣ በዛራሔምላ ምድር የነበሩት ወንድሞቼ እስከአሁን በህይወት እንደሚኖሩ አውቃለሁ። እናም አሁን እደሰታለሁ፤ በማግስቱም ህዝቦቼ ደግሞ እንዲደሰቱ አደርጋለሁ።

፲፭ እነሆም፣ እኛ በላማናውያን ባርነት ስር ነን፣ እናም ልንሸከመው በማይቻል በታላቅ ቀረጥ ᵐእንቀረጣለን። እናም አሁን እነሆ፣ ወንድሞቻችን ከባርነት ወይም ከላማናው ያን እጅ ያስለቅቁናል፣ እናም እኛ የእነ ርሱ ባሮች እንሆናለን፤ ለላማናውያን ግብር ከመክፈል ለኔፋውያን ባርያ መሆን ይሻ ላልና።

፲፮ እናም አሁን፣ ንጉስ ሊምሂ ለጠባቂ ዎቹ አሞንንም ሆነ ወንድሞቹን ከእንግዲህ እንዳያስሩአቸው አዘዘ፣ ነገር ግን በሺምሎን በስተሰሜን ወዳለው ኮረብታ እንዲሄዱና ወንድሞቻቸውን ወደ ከተማይቱ እንዲያ መጡና በዛም ይመገቡና፣ ይጠጡ፣ እን ዲሁም ከጉዞአቸውም ድካም እንዲያርፉ አደረገ፣ ምክንያቱም በብዙ ነገሮች ተሰ ቃይተዋል፣ በረሃብ በጥማትና በድካምም ተሰቃይተዋልና።

፲፯ እናም አሁን፣ እንዲህ ሆነ በማግ ስቱ ንጉሱ ሊምሂ ᵐበቤተመቅደስ በአንድ ነት እራሳቸውን ሰብስበው የሚያነጋግራ ቸውን ያደምጡ ዘንድ በህዝቡ ሁሉ መካ ከል አዋጅን ላከ።

፲፰ እናም እንዲህ ሆነ እራሳቸውን በአ ንድ ላይ በሰበሰቡ ጊዜ እንዲህ በማለት ተና

፭ ᴴ ሞዛያ ፱፡ ፮፣ ፰፣ ፲፱።
፮ ᴴ ᴱ ኔፊ ፭፡ ፰።
፱ ᴴ ᴱ ኔፊ ፭፡ ፰።
ᴴ ᴱ ኦምኒ ፩፡ ፲ᴱ–፲፭።
ᴴ ᴱ ኔፊ ፭፡ ፲ᴱ–፲፭።
ᴴ ᴱ ኔፊ ፭፡ ፲ᴱ–፲፭።

ገራቸው፥ ህዝቤ ሆይ፣ ራሳችሁን አቅኑና ተፅናኑ፤ እነሆም ምንም እንኳን ከንቱ ከነ በሩት ብዙ ትግሎቻችን ብንታገልም፣ በጠ ላቶቻችን ስር ከእንግዲህ የማንሆንበት ጊዜ መጥቷል፣ እና ሩቅ አይደለም፤ ነገር ግን የሚቀረው ትግላችን ወደፈለግነው ውጤት እንደሚያደርሰን አምናለሁ።

፲፱ ስለዚህ፣ ራሳችሁን አቅኑና፣ ተደ ሰቱ፣ እንዲሁም እምነታችሁን የአብርሃ ምና የይስሀቅ፣ እናም የያዕቆብ አምላክ በሆ ነው፣ ደግሞም፣ የእስራኤልን ልጆች ከግ ብፅ ምድር ᵐባወጣው ᵃአምላክና፣ በደረቅ ምድር በቀይ ባህር ውስጥ እንዲጓዙ ባደረ ገው፣ እናም በምድረበዳው ውስጥ እንዳ ይጠፉ ᵐመናን ከዚህ የበለጡ ብዙ ነገሮችን ባደረገላቸው በዚያ እግዚአብሔር እምነታ ችሁን አድርጉ።

፳ እናም እንደገና፣ ይኸው አምላክ አባ ቶቻችንን ከኢየሩሳሌም ምድር ᵐአውጥ ቷቸዋል፣ እናም እስከአሁን ድረስ ህዝቡን ጠብቋል እንዲሁም አስቀምጧል፤ እናም እነሆ፣ በኃጢአታችንና በእርኩሰታችንም የተነሳ ወደባርነት ወስዶናል።

፳፩ እናም በዚህ ቀን ሁላችሁም ምስክ ሮች ናችሁ፣ ዜኒፍ በዚህ ህዝብ ላይ ንጉስ የተደረገው፣ የአባቶቹን ምድር ለመውረስ ᵐጓጉቷልና፤ ስለዚህ በብልጥነትና በተንኮል በማታለል ከንጉስ ዜኒፍ ጋር ስምምነት የገ ባው ንጉስ ላማን የምድሪቷን ክፍል፣ ወይም እንዲሁም የሌሂ-ኔፊ ከተማንና፣ የሼምሎ ንን ከተማ፤ እንዲሁም በዙሪያዋ ያለውን ምድር ንብረት ወደ እጆቹ አሳልፎ ሰጠ—

፳፪ እናም ይህንን ሁሉ እርሱ ያደረገው፣ ይህን ህዝብ በቁጥጥሩ ስር ወይም በባርነት ስር ᵐለማዋል ባለው ብቸኛ ዓላማ ነበር። እናም እነሆ፣ እኛ በዚህ ጊዜ፣ መጠኑም ከበቆሎአችንና ከገብሳችን እንዲሁም ከሁ ሉም አይነት ጥራጥሬዎቻችን ግማሹንና፣ ከከብት መንጋዎቻችን አንድ ሁለተኛውን በግብር ለላማናውያን ንጉስ እንከፍላለን፤ እና እንዲሁም ካሉን ንብረቶቻችንም አንድ ሁለተኛ እንኳን ወይም ህይወታችንን የላ ማናውያንን ንጉስ ይወስድብናል።

፳፫ እናም አሁን፣ ይህ ለመቋቋም አስ ቸጋሪ አይደለምን? እናም ይህስ ስቃያችን ታላቅ አይደለምን? አሁን እነሆ ለማዘንስ ምን ያህል ታላቅ ምክንያት ይኖረናል።

፳፬ አዎን፣ እንዲህ እላችኋለሁ፣ ለሀዘና ችን ምክንያቶቻችን ታላቅ ናቸው፤ እነሆም የተገደሉ እንዲሁም ደማቸው በከንቱ የፈሰ ሰው ወንድሞቻችን ምን ያህል ናቸው፣ እና ያም ሁሉ በክፋት ምክንያት።

፳፭ እነዚህ ሰዎች ወደመተላለፍ ባይወ ድቁ ኖሮ ጌታ ይህ ታላቅ ክፋት በእነርሱ ላይ እንዲሆን አይፈቅድም ነበር። ነገር ግን እነሆ፣ እነርሱ ቃሉን አያደምጡም፣ ነገር ግን በመካከላቸውም ብዙ ደም መፋሰስ እስ ከሚሆን ድረስ፣ በመካከላቸው ጠብ ተነሳ።

፳፮ እናም አዎን በእግዚአብሔር የተመ ረጠውን ኃጢአታቸውን እናም እርኩሰታ ቸውን የነገራቸውንና ብዙ የሚመጡ ነገ ሮችን፣ አዎን፣ የክርስቶስንም መምጣት ቢሆን የተነበየውን የጌታን ᵐነቢይ ገድለ ዋል።

፳፯ እናም እርሱ ክርስቶስ ᵐአምላክ መሆ ኑን የሁሉም ነገር አባት መሆኑን በመናገ ሩም፣ የሰውንም መልክ በራሱ መውሰዱ ንና፣ ይህም ሰው ከመጀመሪያው ጀምሮ የተፈጠረበት ᵃአምሳል መሆኑን፤ ወይም በሌላ አነጋገር ሰው በአምላክ አምሳያ ተፈ ጥሯል፣ ᵃአምላክም በሰው ልጆች መካ ከል ይመጣል፣ እናም በራሱ ላይ ስጋና ደም ይለብሳል፣ እናም በምድር ገፅ ላይ ይሄዳል ስላለ—

፲፱ ᵐ ዘፀአ. ፲፪፡ ፴–፴፭፤ አልማ ፴፯፡ ፳፰።
ᵃ ዘፀአ. ፫፡ ፮፤ ፩ ኔፊ ፲፱፡ ፲።
ᵃ ዘፀአ. ፲፯፡ ፲፭፡ ፴፭፤ ዘኁል. ፲፩፡ ፮–፳፣ ኢ.ያ. ፭፡ ፲፪።
፳ ᵐ ፩ ኔፊ ፪፡ ፩–፱።
፳፩ ᵐ ሞዛያ ፱፡ ፩–፫።
፳፪ ᵐ ሞዛያ ፲፡ ፲፰።
፳፫ ᵐ ሞዛያ ፲፯፡ ፲፪–፳።
፳፮ ᵐ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ።
ᵃ ዘፍጥ. ፩፡ ፳፮–፳፰፤ ኤተር ፫፡ ፲፬–፲፮፤ ት. እና ቃ. ፳፡ ፲፯–፲፰።
ᵃ ሞዛያ ፲፫፡ ፴፫–፴፬፤ ፲፭፡ ፩–፱።

፳፰ እናም አሁን፣ ይህንን በማለቱ፣ ገደሉት፤ እናም በራሳቸው ላይ የእግዚአብሔርን ቁጣ የሚያስከትሉ ከዚህ የበለጡ ብዙ ነገሮችን አደረጉ። ስለዚህ በታላቅ ስቃይ በመመታታቸውና፣ እነርሱ በመታሰራቸው ማን ይደነቃል?

፳፱ እነሆም፣ ጌታ እንዲህ ይላል፣ በመተላለፋቸው ቀን ህዝቤን ″አልረዳም፣ ነገር ግን እንዳይበለፅጉ መንገዱን እከላከላለሁ፤ እናም ስራቸው በፊታቸው የመሰናከያ አለት ይሆንባቸዋል።

፴ እናም እንደገና፣ እርሱ እንዲህ ይላል፥ ህዝቤ ″ቆሻሻን ከዘሩ በአውሎ ነፋስ ገለባን ˡይሰበስባሉ፤ እናም ውጤቱ መርዝ ነው።

፴፩ እናም እንደገና እርሱ እንዲህ ይላል፥ ህዝቤ ቆሻሻውን ከዘሩ ፈጣን የሆነ ጥፋት የሚያመጣውን ″የምስራቁን ንፋስ ያጭዳሉ።

፴፪ እናም አሁን፣ እነሆ፣ የጌታ ቃል ኪዳን ተፈፅሟል፣ እናም እናንተ ተመትታችኋል እንዲሁም ተሰቃይታችኋል።

፴፫ ነገር ግን በሙሉ የልባችሁ ዓላማ ወደ ጌታ ″የምትመለሱ ከሆነ፣ እናም እምነታችሁን በእርሱ ካደረጋችሁ፣ እናም በሙሉ ትጉህ ህሊናችሁ እርሱን ካገለገላችሁ፣ ይህንን ካደረጋችሁ በፈቃዱና በደስታው መሰረት ከባርነት ያወጣችኋል።

ምዕራፍ ፰

አሞን የሊምሂን ህዝብ አስተማረ—ስለ ሀያ አራቱ ያሬዳውያን ሰሌዳዎች ተማረ—የጥንት ታሪኮች በባለራዕዮች መተርጎም ይችላሉ—ከባለራዕይነት የበለጠ ስጦታ የለም። ፻፳፩ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ ንጉስ ሊምሂ ለህዝቡ ንግግሩን ከጨረሰ በኋላ፣ ብዙ ነገሮችን ተናግሯል እናም እኔ ጥቂቶቹን ብቻ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ፅፌአለሁ፤ በዛራሔምላ ምድር የነበሩት ወንድሞቹን በተመለከተ ለህዝቡ ሁሉንም ነገር ነገራቸው።

፪ እናም አሞን በህዝቡ ፊት ቆሞና፣ ዜኒፍ ምድሪቱን ለቆ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ እራሱም እንኳን ከምድሪቱ እስከወጣበት ድረስ የተከናወኑትን ሁሉ እንዲናገር አደረገ።

፫ እናም ደግሞ ንጉስ ቢንያም ያስተማራቸውን የመጨረሻ ቃላት ነገራቸው፣ እናም እርሱ የተናገራቸውን ቃላት ሁሉ ይረዱት ዘንድ ለንጉስ ሊምሂ ህዝብም ገለፀላቸው።

፬ እናም እንዲህ ሆነ ይህን ሁሉ ካደረገ በኋላ፣ ንጉስ ሊምሂ ህዝቡን አሰናበተ፣ እናም እያንዳንዳቸው ወደየቤታቸው እንዲመለሱ አደረገ።

፭ እናም እንዲህ ሆነ ህዝቡ የዛራሔምላን ምድር ለቀው ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ የነበረውን ″ታሪክ የያዙትን ሰሌዳዎች አሞን ያነባቸው ዘንድ በፊቱ እንዲቀርቡ አደረገ።

፮ አሁን፣ አሞን ታሪኩን እንዳነበበ፣ ቋንቋውን መተርጎም እንደሚችሉ ንጉሱ ጠየቀው እናም አሞንም እንደማይችል ነገረው።

፯ እናም ንጉሱ እንዲህ አለው፥ በህዝቤ ስቃይ በማዘኔ፣ ከህዝቤ አርባ ሶስት የሆኑት የዛራሔምላን ምድር ያገኙ ዘንድ፣ ከባርነትም እንዲያስለቅቁን ለወንድሞቻችን አቤት እንልበት ዘንድ ወደ ምድረበዳው እንዲጓዙ አደረግሁ።

፰ እናም እነርሱ ለብዙ ቀናት በምድረበዳ ውስጥ ጠፉ፣ ነገር ግን ትጉህ ነበሩ፣ እናም የዛራሔምላን ምድር አላገኙትም ነበር፣ ነገር ግን በብዙ ውኃዎች መካከል ባለች ምድር አቋርጠው ተጉዘው፣ በሰዎችና፣ በአውሬዎች አጥንት፣ እናም ደግሞ በሁሉም አይነት የግንብ ፍርስራሽ የተሸፈነች ምድር አግኝተው፣ እንደ እስራኤልም ሰራ

፳፱ ሀ ፩ ሳሙ. ፲፪፥፲፭፤
፪ ዜና ፳፬፥፳።
፴ ሀ ቅ.መ.መ. እድፍ፣
እድፍነት።
ለ ገላ. ፮፥፯–፰፤
ት. እና ቃ. ፮፥፴፫።
ቅ.መ.መ. መከር።
፴፩ ሀ ኤር. ፲፰፥፲፯፤
ሞዛያ ፲፪፥፯።
፴፫ ሀ ሞር. ፱፥፯።
፰ ፭ ሀ ሞዛያ ፱–፳፪።

ዊት ብዙ ህዝቦች የነበሯትን ምድር ካገኙ በኋላ ወደዚህች ምድር ተመለሱ።

፱ እናም ለምስክርነት የተናገሯቸው ነገሮች እውነት መሆናቸውን ለማሳየት በፅሁፍ የተሸፈኑ [ሀ]ሀያ አራት ሰሌዳዎችን አቀረቡ፣ እናም እነርሱ ንፁህ ወርቆች ነበሩ።

፲ እናም እነሆ፣ ደግሞ፣ ትልቅ [ለ]ነህስ፣ እንዲሁም መዳብ፣ እናም ፍፁም ጥሩ የሆኑትን [ሐ]ጥሩሮች አመጡ።

፲፩ እናም እንደገና፣ እጀታቸው የጠፉና፣ ስለታቸው ዝጎ የተበላሹ ጎራዴዎችን አመጡ፤ እናም በምድሪቱ ቋንቋውንም ሆነ በሰሌዳዎቹ ላይ ያሉትን ፅሁፎች መተርጎም የሚችል ማንም አልነበረም። እናም እንዲህ እልሃለሁ፥ አንተ መተርጎም አትችልምን?

፲፪ እናም በድጋሚ እንዲህ እልሃለሁ፣ መተርጎም የሚችልስ ማንንም አታውቅምን? ይህ ታሪክ ወደራሳችን ቋንቋ እንዲ ተረጎም እፈልጋለሁና፤ ምናልባት እነዚህ ሰሌዳዎች የመጡባቸው ስለጠፉት ህዝቦች ቅሪት እውቀት ይሰጡናልና፤ ወይንም ምናልባት ስለጠፉት እነዚህ ሰዎች ግንዛቤ ይሰጡን ይሆናልና፤ እናም የመጥፋታቸውን መንስኤ ለማወቅ እፈልጋለሁ።

፲፫ አሁን አሞን እንዲህ አለው፥ ንጉስ ሆይ መዝገቡን [ሀ]መተርጎም ስለሚችለው ሰው በእርግጠኝነት ልነግርህ እችላለሁ፤ ምክንያቱም እርሱ የሚመለከትበትና በጥንት ጊዜ የነበሩትን መዛግብት ሁሉ ለመተርጎም የሚችልበት አለው፣ እናም ይህ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። ነገሮቹም [ለ]ተርጓሚዎች ተብለው ይጠራሉ፣ እናም ካልታዘዘ በስተቀር ማንም ሰው በእነርሱ መመልከት አይችልም፣ አለበለዚያ ማድረግ የሌለበትን ይሻልና፣ ይጠፋል። እናም በእነርሱ ለመመልከት የታዘዘ ሰው [ሐ]ባለራዕይ ተብሎ ይጠራል።

፲፬ እናም እነሆ፣ በዛራሔምላ ምድር ያለው የህዝቡ ንጉስ እነዚህን ነገሮች እንዲሰራ የታዘዘ ነው፣ እናም ይህ ታላቅ ስጦታ ከእግዚአብሔር ያገኘው ነው።

፲፭ እናም ንጉሱ ባለራዕይ ከነቢይ የበለጠ ነው አለ።

፲፮ እናም አሞን ባለራዕይ፣ ገላጭና፣ ደግሞም ነቢይ ነው አለ፤ እናም ከዚህ ይበልጥ ታላቅ የሆነ ስጦታ የእግዚአብሔር ኃይል ከሌለው በቀር ማንም ሰው ሊኖረው አይችልም፤ ነገር ግን ሰው ከእግዚአብሔር የተሰጠ ታላቅ ኃይል ሊኖረው ይችላል።

፲፯ ነገር ግን ባለራዕይ ያለፉ ነገሮችን ሊያውቅ ይችላል፣ ደግሞም ሊሆኑ የሚችሉትን ነገሮች ሊያውቅ ይችላል፣ እናም በእነርሱ አማካይነት ሁሉም ነገሮች ይገለጣሉ፣ ወይም ሚስጥሮች ይታወቃሉ፣ የተደበቁ ነገሮች ወደብርሃን ይመጣሉ፣ እናም የማይታወቁ ነገሮች በእነርሱ እንዲታወቁ ይሆናሉ፤ እናም ደግሞ በእነርሱ ካልሆኑ በቀር የማይታወቁትን ነገሮች እንዲታወቁ ይደረጋሉ።

፲፰ በዚህም እግዚአብሔር ሰው በእምነት ታላቅ ድንቅ ነገሮችን ይሰራ ዘንድ ዘዴውን አቅርቦለታል፤ ስለዚህ እርሱም ለእንደእርሱ አይነት ህያው ፍጡር ጠቃሚ ይሆናል።

፲፱ እናም አሁን፣ አሞን እነዚህን ቃላት መናገሩን እንደጨረሰ ንጉሱ እጅግ ተደሰተና፣ ለእግዚአብሔር እንዲህ ሲል ምስጋናውን አቀረበ፥ እነዚህ ሰሌዳዎች ታላቅ [ሀ]ሚስጥር እንደያዙ ጥርጥር የለውም፣ እናም እነዚህ ተርጓሚዎች ለሰዎች ልጆች ሁሉንም እንደዚህ አይነት ሚስጥሮች ለማብራራት ሲባል ያለጥርጥር ተዘጋጅተዋል።

፳ አቤቱ የጌታ ስራ እንዴት ድንቅ ነው፤ እናም ከህዝቦቹስ ጋር ምን ያህል ጊዜ ይሰቃያል፤ አዎን፣ የሰው ልጅ ግንዛቤስ እንዴት ዕውርና የማይደረስበት ነው፣ ምክንያቱም ጥበብን አይሹምና፣ [ሀ]እርሷም በእነርሱ ላይ እንድትገዛ አይፈልጉምና!

፱ *ሀ* ኤተር ፩፡፩–፪።
፲ *ሀ* ኤተር ፲፡፳፫።
ለ ኤተር ፲፭፡፲፭።
፲፫ *ሀ* ሞዛያ ፳፰፡፲–፲፯።
ለ ቅ.መ.መ. ኡሪም እና ቱሚም።
ሐ ቅ.መ.መ. ባለራዕይ።
፲፱ *ሀ* ኤተር ፫፡፳፩–፳፰፤ ፪፡፱–፲፡ ማቴ. ፲፩፡፲፱።
፳ *ሀ* ይህም ጥበብ በዕብራውያን እና በግሪክ ቋንቋ የሴት ስም ነው ማለት ነው። ምሳ. ፱፡፩፤ ማቴ. ፲፩፡፲፱።

፳፩ አዎን፣ እነርሱ ከእረኛው እንደሸሸው እንዳልተገራው መንጋ ናቸው፣ ይበተና ሉም፣ ይነዳሉም፣ እናም በጫካ አውሬዎ ችም ይበላሉ።

የዜኒፍ መዝገብ—የዛራሔምላን ምድር ለቀው ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ ከላማናውያን እጅ እስከተለቀቁበት ጊዜ ድረስ ያለው የህዝቡ ታሪክ።

ከምዕራፍ ፱ እስከ ምዕራፍ ፳፪ አጠቃሎ የያዘ።

ምዕራፍ ፱

ዜኒፍ የሌሂ-ኔፊን ምድር እንዲወርሱ ከዛራሔምላ ቡድንን መራ—የላማናውያን ንጉስ ምድሪቱን እንዲወርሱ ፈቀደላቸው—በላማናውያንና በዜኒፍ ህዝብ መካከል ጦርነት ሆነ። ፪፲–፲፱፲፮ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እኔ ዜኒፍ፣ በኔፋውያን ቋንቋዎች ሁሉ በመማሬ፣ እናም ᐸስለኔፊ ምድር ወይም የመጀመሪያው የአባታችን የውርስ ምድር በማወቄ፣ እናም የእኛ ወታደሮች በእነርሱ ላይ መጥተው ያጠፏቸው ዘንድ ኃይላቸ ውን ለመሰለል በላማናውያን መካከል ሰላይ ሆኜ ተላኩ፣ ነገር ግን በእነርሱ መካከል ጥሩ የሆነን ነገር በተመለከትኩ ጊዜ እንዳይጠፉ ፈለግሁ።

፪ ስለዚህ፣ መሪያችን ከእነርሱ ጋር ሰም ምነት እንዲፈፅም በመፈለጌ በምድረበዳ ውስጥ ከወንድሞቼ ጋር ተከራከርኩ፤ ነገር ግን እርሱ ጨካኝና ደም የተጠማ ሰው በመ ሆኑ እንድገደል ወሰነብኝ፤ ነገር ግን በብዙ ደም መፋሰስ ዳንኩ፤ ምክንያቱም ብዙ ቁጥር ያላቸው ወታደሮች በምድረበዳ እስ ከሚጠፉ ድረስ አባት ከአባት፣ እናም ወን ድም ከወንድም ተዋግተዋልና፤ እናም እኛ የተረፍነው የሞቱትን ታሪክ ለሚስቶቻች ውና ለልጆቻቸው ለመተረክ ወደዛራሔምላ ምድር ተመለስን።

፫ እናም፣ የአባቶቻችንን ምድር ለመ ውረስ በጣም በመጓጓት፣ ምድሪቱን ለመ ውረስ የፈለጉት ሁሉ ሰበሰብኩኝ፣ እናም ወደ ምድሪቱ ለመሄድ ጉዞአችንን በድጋሚ ወደ ምድረበዳ ጀመርን፤ ነገር ግን በረሃብና በታላቅ ስቃይ ተመታን፣ ምክንያቱም ጌታ አምላካችንን ለማስታወስ ዘግይተናልና።

፬ ይሁን እንጂ፣ ብዙ ቀናት በምድረበዳ ውስጥ ከተዘዋወርን በኋላ፣ ለአባቶቻችን ምድር ቅርብ በሆነው ወንድሞቻችን በተ ገደሉበት ስፍራ ድንኳናችንን ተከልን።

፭ እናም እንዲህ ሆነ የንጉሱን ዓላማ አውቅ ዘንድ፣ እናም ከህዝቤ ጋር መሄ ድና፣ ምድሪቱን በሰላም መውረስ እን ችል እንደሆነ አውቀው ዘንድ ከአራቱ ሰዎቼ ጋር በድጋሚ ወደከተማው፣ ወደ ንጉሱ ሄድኩኝ።

፮ እናም ወደ ንጉሱ ሔድኩ፣ እናም የሌሂ-ኔፊን ምድር እንዲሁም የሼምሎ ንን ምድር እይዘው ዘንድ ከእኔ ጋር ቃል ኪዳን ገባ።

፯ እናም ደግሞ የእርሱ ህዝብ ምድሪ ቱን ለቀው መውጣት እንዳለባቸው አዘዘ፣ እናም እኔና ህዝቤ ምድሪቱን ለመያዝ ሄድን።

፰ እናም ህንፃዎችን መገንባትና፣ የከተ ማውን ግንብ፣ አዎን፣ እንዲሁም የሌሂ-ኔፊ ከተማ ግንቦችንና የሼምሎንን ከተማ መጠገን ጀመርን።

፱ እናም አዎን፣ በሁሉም ዓይነት ዘሮች እንኳን፣ በበቆሎ ዘርና፣ በስንዴ፣ በገብ ስም፣ በኒአስም፣ በሺአምም፣ እንዲሁም በሁሉም ዓይነት የፍራፍሬ ዘሮች ምድሪ ቱን ማረስ ጀመርን፤ እናም በምድሪቱ ላይ መራባትና መበልፀግ ጀመርን።

፲ አሁን ንጉስ ላማን ህዝቤን ወደ ባርነት ᐸለማምጣት፣ እኛ የያዝነውን ምድር የሰ ጠው በጮሌነቱና በብልጠቱ ነው።

፲፩ ስለዚህ እንዲህ ሆነ በምድሪቱ ላይ ለአ

ስራ ሁለት ዓመታት ከኖርን በኋላ፣ ንጉስ
ላማን መቁነጥነጥ ጀመረ፣ ይህም የሆነበት
እንዳያይሉባቸው እናም ወደባርነት እንዳ
ያመጡዋቸው ህዝቤ በምድሪቱ እየበረቱ
በመሄዳቸው ነበር።
፲፪ አሁን እነርሱ ሰነፍና [ሀ]ጣዖት አምላኪ
ነበሩ፣ ስለዚህ እኛ በእጆቻችን በሰራነው
እራሳቸውን ያንደላቅቁ ዘንድ፣ አዎን፣
በሜዳችን መንጋዎች እራሳቸውን ይመ
ግቡ ዘንድ፣ በባርነት ስር ሊያደርጉን ፈል
ገው ነበር።
፲፫ ስለዚህ እንዲህ ሆነ ንጉስ ላማን ህዝቡ
ከህዝቤ ጋር ይከራከር ዘንድ ማወክ ጀመረ፤
ስለዚህ በምድሪቱ ጦርነትና ፀብ ተጀመረ።
፲፬ በኔፊ ምድር በአስራ ሶስተኛው የን
ግስና ዓመቴ፣ በሼምሎን የደቡብ ክፍል፣
ህዝቤ መንጋውን ውሃ ሲያጠጡና ሲመ
ግቡ፣ እናም መሬታቸውን ሲያርሱ ብዙ
ላማናውያን በአንድነት መጥተው እነርሱን
መግደልና መንጋዎቻቸውንና በቅሎዎቻ
ቸውንም መውሰድ ጀመሩ።
፲፭ አዎን፣ እናም እንዲህ ሆነ ያልተያዙት
ሁሉ ወደ ኔፊ ከተማም ጭምር ሸሹ፣ እናም
እኔ እንድከላከላቸውም ፈለጉኝ።
፲፮ እናም እንዲህ ሆነ በቀስትና፣ በወ
ስፈንጥርና፣ በጎራዴ፣ እናም በሻሙላ፣
በቅስትና፣ በወንጭፍ፣ እንዲሁም መስ
ራት በምንችለው በሁሉም ዓይነት መሳሪ
ያዎች ሁሉ እንዲታጠቁ አደረኩኝ፣ እናም
እኔና ህዝቤ ከላማናውያን ጋር ለመዋጋት
ሄድን።
፲፯ አዎን፣ በጌታ ጥንካሬን ከላማናውያን
ጋር ለመዋጋት ሄድን፤ እኔና ህዝቤ ከጠላቶ
ቻችን እጅ ያወጣን ዘንድ በኃይል ወደ ጌታ
ጮህን፣ የአባቶቻችንን የዳኑበትን ለማስታ
ወስ ነቅተናልና።
፲፰ እናም እግዚአብሔር ጩኸታችንን
[ሀ]ሰማ፣ ለፀሎታችንም መልስ ሰጠ፤ እናም
በኃይሉ ወደፊት ሄድን፣ አዎን፣ በላማና
ውያን ላይ ሄድን፣ እናም በአንድ ቀንና
ሌሊት ሶስት ሺህ አርባ ሶስት ሰዎችን ገደ
ልን፤ ከምድራችንም እስክናስወጣቸው
ድረስ ገደልናቸው።
፲፱ እናም፣ እኔ፣ በራሴ እጅ ሙታኖቻቸ
ውን ለመቅበር ረዳሁ። እናም እነሆ ሁለት
መቶ ሰባ ዘጠኝ ወንድሞቻችን ስለተገደ
ሉብን ሀዘናችንና ልቅሶአችን መሪር ነበር።

ምዕራፍ ፲

ንጉስ ላማን ሞተ—ህዝቡም አረመኔና የሚያስፈሩ እንዲሁም በሐሰት ባህል የሚያምኑ ነበሩ—ዜኒፍና ህዝቡ ድል አደረጉአቸው። ከ፻፹፯–፻፷ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ በድጋሚ መንግ
ስቱን መመስረት ጀመርን፣ እናም እን
ደገና ምድሪቱን በሰላም መውረስ ጀመ
ርን። እናም ላማናውያን በድጋሚ ከህዝቤ
ጋር ለመዋጋት በሚመጡበት ጊዜ ለህዝቤ
መሳሪያ ይኖራቸው ዘንድ ከሁሉም ዓይ
ነት የተሰሩ የጦር መሳሪያዎች እንዲኖራ
ቸው አደረግሁ።
፪ እናም ላማናውያን ሳናውቀው መጥተው
እንዳያጠፉን በምድሪቱ ዙሪያ ጠባቂዎችን
አስቀመጥሁ፤ እናም ህዝቤንና መንጋዎቼን
እንደዚህ ጠበቅሁ፣ እናም በጠላቶቻችን
እጅ እንዳይወድቁም ጠበቅኋቸው።
፫ እናም እንዲህ ሆነ ለብዙ ዓመታት የአ
ባቶቻችንን ምድር ወረስን፤ አዎን፣ እንዲ
ሁም ለሀያ ሁለት ዓመታት።
፬ እናም ሰዎች መሬቱን እንዲያርሱ፣
እናም ሁሉንም ዓይነት [ሀ]እህልና፣ ሁሉ
ንም ዓይነት ፍራፍሬዎች እንዲያሳድጉ
አደረግሁ።
፭ እናም ሴቶች እንዲፈትሉ፣ እንዲደክ
ሙም፣ እንዲሰሩም፣ እናም ሁሉንም ዓይ
ነት ናይለን [ሀ]ጨርቅ፣ አዎን፣ ሁሉንም ዓይ
ነት ልብሶች በመስራት እርቃናችንን እንሸ
ፍንበት ዘንድ እንዲሰሩ አደረግሁ፤ እናም
እንደዚህ በምድሪቱ ላይ በለፀግን—እንደ

፲፪ ሀ ኢኖስ ፩፥ ፳።
ቅ.መ.መ. ጣኦት አምላኪ።
፲፰ ሀ ሞዛያ ፳፱፥ ፳።
፲ ፬ ሀ ሞዛያ ፱፥ ፱።
፭ ሀ አልማ ፩፥ ፳፱።

ዚህም በምድሪቱ ላይ ለሀያ ሁለት ዓመታት ያለማቋረጥ ሰላምን አገኘን።

፮ እናም እንዲህ ሆነ ንጉስ [ሀ]ላማን ሞተና፣ በቦታው ልጁ ነገሰ። እናም ህዝቡን ከህዝቤ ጋር በአመፅ ማወክ ጀመረ፤ ስለዚህ እነርሱ ለጦርነት መዘጋጀትና፣ ከህዝቤ ጋር ለመዋጋት መምጣት ጀመሩ።

፯ ነገር ግን ዝግጅታቸውን እንዳውቅ፣ በህዝቤ ላይ እንዳይመጡና እንዳያጠፉአቸው ከእነርሱ እጠብቃቸው ዘንድ [ሀ]በሽምሎን ምድር ዙሪያ ሰላዮቼን ላክሁ።

፰ እናም እንዲህ ሆነ [ሀ]በቀስትም፣ በጦርም፣ በሳንጃና ሻምላም፣ በድንጋይም፣ እንዲሁም በወንጭፍ [ለ]በታጠቁ ብዙ ሰራዊቶቻቸው ከሼምሎን ምድር በስተሰሜን በኩል መጡ፤ እናም ራሳቸው በመላጨቱ ባዶ ነበር፣ እናም በወገባቸው ላይ የቆዳ መቀነት ታጥቀው ነበር።

፱ እናም እንዲህ ሆነ ከህዝቤ ሴቶችና ህፃናት በምድረበዳው እንዲደበቁ አደረግሁ፤ እናም ደግሞ መሳሪያዎቻቸውን ይዘው መምጣት የሚችሉ ሽማግሌዎች ሁሉና ደግሞ መሳሪያዎቻቸውን ይዘው መምጣት የሚችሉ ወጣት ወንዶች ከላማናውያኖች ጋር ለመዋጋት በአንድ ላይ ራሳቸውን እንዲሰበስቡ አደረግሁ፤ እናም እያንዳንዱን ሰው እንደ ዕድሜው በደረጃው አሰለፍኳቸው።

፲ እናም እንዲህ ሆነ ከላማናውያን ጋር ለመዋጋት ሄድን፤ እናም እኔም እንኳን በእርጅና ዕድሜዬ፣ ከላማናውያን ጋር ለመዋጋት ሄድኩ። እናም እንዲህ ሆነ በጌታ [ሀ]ጥንካሬ ለጦርነት ሄድን።

፲፩ አሁን፣ ላማናውያን የጌታንም ሆነ የጌታን ጥንካሬ በተመለከተ ምንም አያውቁም፣ ስለዚህ በራሳቸው ጥንካሬ ተመክተው ነበር። ይሁን እንጂ እንደሰዎች ጥንካሬ ጠንካራ ነበሩ።

፲፪ እነርሱም [ሀ]አረመኔና የሚያስፈሩ እንዲሁም ደም የተጠሙ፣ ይህም በሆነው—ከኢየሩሳሌም ምድር በአባቶቻቸው ክፋት እንደወጡ፣ እናም በምድረበዳ በወንድሞቻቸው ክፉ እንደተደረገባቸው፣ እናም ደግሞ ባህሩን በሚያቋርጡበት ጊዜ ክፉ እንደተደረገባቸው በማመን፣ በአባቶቻቸው [ለ]ባህል የሚያምኑ ነበሩ፤

፲፫ እናም በድጋሚ ባህሩን ከተሻገሩ በኋላ [ሀ]በመጀመሪያው የውርስ አገራቸው በነበሩ ጊዜ ክፉ ተደርጎባቸው ነበር፣ እና ይህ ሁሉ የሆነው ኔፊ ከሁሉም በበለጠ የጌታን ትዕዛዛት ለመጠበቅ ታማኝ በመሆኑ—ስለዚህ እርሱ በጌታ [ለ]የተደገፈ ነበር፣ ጌታም ፀሎቱን ሰምቶን መልስ ሰጥቶታልና፣ እናም በምድረበዳ ጉዞአቸው መሪነትን ወስዷልና።

፲፬ እናም ወንድሞቹ በእርሱ ተቆጡ፣ ምክንያቱም የጌታን አድራጎት [ሀ]አልተረዱምና፣ ውኃውንም ደግሞ ሲያቋርጡ [ለ]ተቆጥተው ነበር፣ ምክንያቱም በጌታ ላይ ልባቸውን አጠጥረው ነበርና።

፲፭ እናም እንደገና፣ በቃል ኪዳኑ ምድር በደረሱበት ጊዜ የህዝቡን [ሀ]አገዛዝ ከእጃችን ወስዷል በማለትበእርሱ ተቆጥተው ነበር፤ እናም ሊገድሉት ፈለጉ።

፲፮ እናም እንደገና፣ ጌታ እንዳዘዘው ወደ ምድረበዳ በመሸሹ፣ እናም በነሃስ ሰሌዳዎች ላይ የተፃፉትን [ሀ]መዝገቦች በመውሰዱ [ለ]ዘርፎናል በማለት ተቆጥተው ነበር።

፲፯ እናም እንደዚህ ልጆቻቸው እንዲጠሉአቸውና እንዲገድሉአቸው፣ እናም እንዲሰርቋቸውና እንዲዘርፏቸው፣ እናም እነርሱን ለማጥፋት የሚችሉትን ሁሉ እንዲያደርጉ አስተምረዋቸዋል፤ ስለዚህ በኔፊ ልጆች ላይ ዘለዓለማዊ ጥላቻ አላቸው።

፲፰ ለዚህም ዋና ምክንያት ንጉስ ላማን ህዝቤን ያጠፋቸው ዘንድ ወደዚህ ምድር

፮ሀ ሞዛያ ፱፥፲–፲፩፤ ፳፬፥፫።
፯ሀ ሞዛያ ፲፩፥፲፪።
፰ሀ አልማ ፫፥፬–፭።
ለ ጄረም ፩፥፰።
፲ሀ ቅ.መ.መ. መታመን።
፲፪ሀ አልማ ፲፯፥፲፬።
ለ ፪ ኔፊ ፭፥፩–፫።
፲፫ሀ ፩ ኔፊ ፲፰፥፳፫።
ለ ፩ ኔፊ ፲፯፥፴፭።
፲፬ሀ ፩ ኔፊ ፲፭፥፯–፲፩።
ለ ፩ ኔፊ ፲፰፥፲–፲፩።
፲፭ሀ ፪ ኔፊ ፭፥፫።
፲፮ሀ ፪ ኔፊ ፭፥፲፪።
ለ አልማ ፳፥፲፤ ፲፫።

እንዳመጣ በሚያባብል በውሸት ተንኮል
እናም በመልካም ቃሉ አታለለኝ፤ አዎን፣
እናም በምድሪቱ ላይ ለብዙ ዓመታት ተሰ
ቃየን።

፲፱ እናም አሁን፣ እኔ ዜኒፍ፣ ላማናው
ያንን በተመለከተ ለህዝቤ እነዚህን ነገሮች
ሁሉ ከተናገርኩ በኋላ፣ እምነታቸውን
በጌታ ጥለው ባላቸው ኃይል ወደ ጦርነቱ
እንዲሄዱ አበረታታኋቸው፤ ስለዚህ ፊት
ለፊት ከእነርሱ ጋር ተዋጋን።

፳ እናም እንዲህ ሆነ በድጋሚ ከምድራ
ችን አስወጣናቸው፣ እናም በከፍተኛ ግድያ
ጨፈጨፍናቸው፤ እንዲያውም በጣም ብዙ
ሆነው አልቆጠርናቸውም።

፳፩ እናም እንዲህ ሆነ ወደ ራሳችን ምድር
በድጋሚ ተመለስን፣ እናም ህዝባችን በድ
ጋሚ መንጋዎቻቸውን መጠበቅና፣ መሬ
ታቸውን ማረስ ጀመሩ።

፳፪ እናም አሁን፣ እኔ በማርጀቴ፣ መን
ግስቱን ከልጆቼ ለአንዱ ሰጠሁ፤ ስለዚህ
ከእንግዲህ ምንም አልናገርም። እናም ጌታ
ህዝቤን ይባርክ። አሜን።

ምዕራፍ ፲፩

*ንጉስ ኖህ በክፉት ገዛ—ከሚስቶቹና
ከዕቁባቶቹ ጋር በቀበጠ ብልሹ ኦኖኒር
ፈነጠዘ—አቢናዲ ህዝቡ ለባርነት እን
ደሚወሰድ ተነበየ—ንጉስ ኖህ ሀይወቱን
ሊያጠፋ ፈለገ። ከ፳፫–፳፱ ም.ዓ. ገደማ።*

፩ እናም አሁን እንዲህ ሆነ ዜኒፍ ከልጆቹ
አንዱ ለሆነው ለኖህ መንግስቱን ሰጠው፤
ስለሆነም ኖህ በእርሱ ቦታ መንገስ ጀመረ፤
እናም በአባቱ መንገድ አልተራመደም
ነበር።

፪ እነሆም፣ የጌታን ትዕዛዛት አልጠበቀም
ነበር፣ ነገር ግን በልቡ ፍላጎት ይራመድ
ነበር። እናም ብዙ ሚስቶችና [ሀ]ዕቁባቶች
ነበሩት። እናም ህዝቡም ኃጢያትን እንዲ
ፈፅሙና፣ በጌታ ፊት ርኩስ የሆነውን እን
ዲሰሩ [ለ]አደረገ። አዎን፣ እናም [ሐ]ዝሙት
ንና ሁሉንም ዓይነት ኃጢአቶችን ፈፀሙ።

፫ ባላቸው ንብረት ላይ ሁሉ፣ አንድ
አምስተኛ ከወርቃቸውና፣ ከብራቸው፣
እናም አንድ አምስተኛ [መ]ከዚፋቸው፣ ከመ
ዳባቸውም፣ ከነሃሳቸውና ከብረታቸውም፣
እናም ከሰቡ ጠቦቶቻቸው አንድ አምስተ
ኛው፣ ደግሞም ከእህላቸው ሁሉ አንድ
አምስተኛው ላይ ቀረጥ መደበባቸው።

፬ እናም እነዚህን በሙሉ የወሰደው ሚስ
ቶቹንና፣ ዕቁባቶቹን፣ ደግሞም ካህናቱን፣
እንዲሁም የእነርሱን ሚስቶችና ዕቁባቶችን
ለመርዳት ነበር፤ እንደዚህም የመንግስቱ
ንም ጉዳዮች ለወጣቸው።

፭ በአባቱ የተሾሙትን ካህናት ሁሉ ሻራ
ቸው፣ እናም በልባቸው ኩራት ያበጡትን
አዳዲሶች በምትካቸው ሾማቸው።

፮ አዎን፣ እናም ለስንፍናቸውና፣ ለጣኦት
አምላኪነታቸው፣ እናም ለዝሙታቸው፣
ንጉስ ኖህ በህዝቡ ላይ ባደረገው ቀረጥ
ተደግፈዋል፤ እንደዚህ ነበር ህዝቡ ጥፋ
ትን ለመደገፍ በጣም የሰሩት።

፯ አዎን፣ እናም ደግሞ እነርሱ ጣኦት
አምላኪ ሆነው ነበር፣ ምክንያቱም በንጉ
ሱና በካህናቱ ከንቱና የሸንገላ ቃላት ተታ
ለው ነበር፤ እነርሱም ከንቱ የሆኑትን ነገ
ሮች ይናገሩአቸው ነበርና።

፰ እናም እንዲህ ሆነ ንጉስ ኖህ ያማሩና
ሰፊ ህንፃዎችን ገነባ፤ እናም በማለፊያ የእ
ንጨት ስራዎችና በሁሉም ዓይነት ውድ
ነገሮች፣ በወርቅም፣ በብርም፣ በብረትም፣
በነሀስም፣ እንዲሁም በዚፍና በመዳብ አስ
ጌጣቸው።

፱ እናም ደግሞ ለራሱ ትልቅ ቤተ መን
ግስትንና በመካከሉ ዙፋንን ሰራ፣ ሁሉም
ማለፊያ እንጨት እናም በወርቅና በብር፣
እንዲሁም በውድ ነገሮች ያጌጡ ነበር።

፲ እናም ደግሞ ሰራተኞቹ በቤተ መቅደሱ

፲፩ ፪ *ሀ* ያዕቆ. ፫፡፭።
ለ ፩ ነገሥ. ፲፪፡፲፩–፲፭፣
ሞዛያ ፳፱፡ ፴፩።
ሐ ፪ ኔፊ ፳፮፡፲፩።
መ *ሀ* ዕብ. የተገናኙ ቃላት። ቅፅል፣
“የሚያንጸባርቅ”፤ ግስ፣
“መሸፈን ወይም በብረት
መሸፈን።”

ግንብ ክልል ውስጥ ከማለፊያ እንጨትና መዳብ እንዲሁም ከነሀስ ሰራቸውን እን ዲሰሩ አደረገ።

፲፭ እናም ከሌሎች መቀመጫዎች ሁሉ በላይ የሆነው ለሊቀ ካህናት የተዘጋጀውን መቀመጫ በንፁህ ወርቅ አስጌጠው፤ እናም ውሸትንና ከንቱ ቃላትን ለህዝባቸው ሲና ገሩ ሰውነታቸውንና ክንዶቻቸውን በላ ያቸው ላይ ያሳርፉበት ዘንድ በፊታቸው መደገፊያን ገነቡላቸው።

፲፮ እናም እንዲህ ሆነ በቤተ መቅደሱ አጠገብ ረጅም [a]ሠገነት ገነባ፤ አዎን፣ በጣም ከፍ ያለ ግንብ፣ በላዩ ላይ በመቆም የሻምሎን ምድር ለማየት የሚያስችል ከፍታ ያለውን፤ እናም ደግሞ በላማናው ያን የተያዘውን የሻምሎን ምድር፤ እናም በዙሪያው ያሉትን ቦታዎች ሁሉ መመል ከት የሚችልበትን ግንብ ሠራ።

፲፯ እናም እንዲህ ሆነ በሼምሎን ምድር ብዙ ህንፃዎች እንዲገነቡ አደረገ፣ እናም ታላቅ ግንብ የኔፊ ልጆች ከምድሪቱ ሸሽ ተው በወጡበት ጊዜ ማረፊያቸው በነበ ረው በሼምሎን በስተሰሜን ኮረብታው ላይ እንዲገነባ አደረገ፤ እናም እንደዚህም ነበር በቀረጥ ከህዝቡ ባካበተው ሀብት የሰራው።

፲፰ እናም እንዲህ ሆነ ልቡን በሃብቶች ላይ አደረገ፣ እናም ከሚሰቶቹና ከዕቁባቶቹ ጋር በቀበጠ ብልሹ ህይወት ጊዜውን አሳለፈ፤ እናም ካህናቱም ደግሞ እንደዚሁ ከጋለሞ ታዎች ጋር ጊዜያቸውን አሳለፉ።

፲፱ እናም እንዲህ ሆነ በምድሪቱ ዙሪያ ወይን አትክልቶችን ተከለ፤ የወይን መጭመቂያንም ሰራ፤ ወይን ጠጅንም በብ ዛት ሰራ፤ እናም በዚህ ምክንያት እርሱና ህዝቡ [b]የወይን ጠጅ ጠጪ ሆኑ።

፲፯ እናም እንዲህ ሆነ የትንሽ ቁጥር ህዝ ቦቹ በሜዳው ላይ ከብቶቻቸውን በሚጠብ ቁበት ጊዜ ላማናውያን በምድሩ ላይ ሊገ ድሉአቸው መምጣት ጀመሩ።

፲፯ እናም ንጉስ ኖህ እነርሱን ለማባረር ጠባቂዎችን በምድሪቱ ላከ፤ ነገር ግን በቂ ቁጥር አልላከም ነበር፣ እናም ላማናውያን በእነርሱ ላይ መጡና ገደሏቸው፣ እናም ብዙ መንጋዎቻቸውን ከምድሪቱ አባረሩ። እንደዚህም ላማናውያን እነርሱን ማጥፋት እናም ጥላቻቸውን በእነርሱ ላይ መለማ መድ ጀመሩ።

፲፰ እናም እንዲህ ሆነ ንጉስ ኖህ ወታደሮ ቹን ላከባቸውና፣ ወደ ኋላ ተመለሱ፣ ወይ ንም ለጊዜው ወደ ኋላ ተመለሱ፤ ስለዚህ በዘረፉት ተደስተው ተመለሱ።

፲፱ እናም አሁን፣ በዚህ በታላቁ ድል ምክንያት በልባቸው ኩራት ተሞልተው ነበር፤ በራሳቸውም ጥንካሬ እንዲህ በማ ለት፥ የእነርሱ ሀምሳዎች የላማናውያንን ሺህ መቋቋም እንደሚችሉ [c]ፎከሩ፤ እናም በደምና በወንድሞቻቸው ደም መፋሰስ ተደሰቱ፣ ይህም በንጉሳቸውና በካህናቶ ቻቸው ክፋት የተነሳ ነው።

፳ እናም እንዲህ ሆነ በእነርሱ መካከል ስሙ [d]አቢናዲ የሚባል አንድ ሰው ነበር፤ እርሱ በመካከላቸው እየሄደም እንዲህ በማለት ትንቢት መናገር ጀመረ፤ እነሆ ጌታ እንዲህ ይላል፤ እናም እንዲህ በማለት አዞኛል፥ ሂድና ለዚህ ህዝብ ጌታ እንዲህ ብሎአል በላቸው—ለዚህ ህዝብ ወዮለት፣ እርኩሰታቸውንና፣ ኃጢአታቸውን እን ዲሁም ዝሙታቸውን አይቻለሁና፤ እናም ንስሃ ካልገቡ በቁጣዬ እጎበኛቸዋለሁ።

፳፩ እናም ንስሃ ካልገቡና ወደ ጌታ አም ላካቸው ካልተመለሱ፣ እነሆ፣ በጠላቶቻ ቸው እጅ እንዲወድቁ አደርጋለሁ፤ አዎን፣ እናም [e]በባርነት ስር ይሆናሉ፤ እናም በጠ ላቶቻቸው እጅ ይሰቃያሉ።

፳፪ እናም እንዲህ ይሆናል እኔ ጌታ አም ላካቸው እንደሆንኩና፣ [f]ቀናተኛ አምላክ መሆኔን፣ የህዝቤን ጥፋት የምጎበኝ እንደ ሆንኩ ያውቃሉ።

፲፪ *a* ሞዛያ ፲፱፡፭–፮።
፲፭ *b* ቅ.መ.መ. የጥበብ ቃል።
፲፱ *c* ት. እና ቃ. ፫፡፬።
ቅ.መ.መ. ኩራት።
፳ *d* ቅ.መ.መ. አቢናዲ።
፳፩ *e* ሞዛያ ፲፪፡፪፤ ፳፡፳፩፤
፳፩፡፲፫–፲፭፤
፳፫፡፳፩–፳፫።
፳፪ *f* ዘፀአ. ፳፡፭፤
ዘዳግ. ፮፡፲፭፤
ሞዛያ ፲፫፡፲፫።

፳፫ እናም እንዲህ ይሆናል፣ ይህ ህዝብ ንስሃ ካልገባ እናም ወደ ጌታ አምላካቸው ካልተመለሱ ወደ ባርነት ይሄዳሉ፤ እናም ሁሉን ከሚገዛው ጌታ እግዚአብሔር በቀር ማንም አያላቅቃቸውም።

፳፬ አዎን፣ እናም እንዲህ ይሆናል፣ ወደ እኔ በሚጮሁበትም ጊዜ ጩኸታቸውን ለመስማት ᵐእዘገያለሁ፤ አዎን እናም በጠላቶቻቸው እንዲመቱ እፈቅዳለሁ።

፳፭ እናም ማቅ ለብሰው፣ አመድ ነስንሰው ንስሃ ካልገቡ እንዲሁም ወደ ጌታ አምላካቸው በኃይል ካልጮሁ በስተቀር፣ ፀሎታቸውን ᵐአልሰማም፣ ወይም ከስቃያቸው አላላቅቃቸውም፤ እናም ጌታ እንዲህ ይላል፣ እንዲህም አዞኛል።

፳፮ አሁን እንዲህ ሆነ አቢናዲ ይህንን ቃል ለእነርሱ በተናገረበት ጊዜ ተቆጡበት፣ እናም ህይወቱን ሊያጠፉ ፈለጉ፤ ነገር ግን ጌታ ከእጃቸው አዳነው።

፳፯ አሁን ንጉስ ኖህ አቢናዲ ለህዝቡ የተናገረውን ቃላት በሰማ ጊዜ እርሱም ደግሞ ተቆጣ፤ እናም እንዲህ አለ፡ አቢናዲ ማን ነው፣ በእኔና በህዝቤ የሚፈርድ፣ ወይም በህዝቤ ላይ ታላቅ ስቃይን የሚያመጣው ጌታስ ᵐማን ነው?

፳፰ አቢናዲን እገድለው ዘንድ እንድ ታመጡት አዛለሁ፣ ምክንያቱም ህዝቦቼ አንዱ በአንዱ ላይ ተቆጥቶ ይታወክ ዘንድ እናም በህዝቤም መካከል ፀብ ለማንሳት እነዚህን ነገሮች ተናግሯልና፤ ስለዚህ እርሱን እገድለዋለሁ።

፳፱ አሁን የህዝቡ ᵐዐይን ታውሯል፤ ስለዚህ በአቢናዲ ቃላት ላይ ልባቸውን ᵃአጠቀረዋል፤ እናም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እርሱን ለመውሰድ ሞክረዋል። እናም ንጉስ ኖህ በጌታ ቃል ላይ ልቡን አጠጠረም፣ ለመጥፎ ስራውም ንስሃ አልገባም።

ምዕራፍ ፲፱

አቢናዲ የህዝቡን ጥፋትና የንጉስ ኖህን ሞት በመተንበዩ ታሰረ—የሀሰት ካህናት ቅዱስ መፅሐፍትን ጠቀሱ እናም የሙሴንም ህግ ለመጠበቅ አስመሰሉ—አቢናዲ እነርሱን አስርቱን ትዕዛዛት ማስተማር ጀመረ። በ፲ዓ.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ ከሁለት ዓመታት በኋላ አቢናዲ እንዳያውቁት ሆኖ በመካከላቸው ተደብቆ መጣ፣ እናም እንዲህ በማለት በመካከላቸው መተንበይ ጀመረ፡ ጌታ እንዲህ ሲል አዞኛል—አቢናዲ ወደ ህዝቦቼ ሂድና ተንብይ፣ በእኔ ቃላት ላይ ልባቸውን አጠጥረዋልና፤ ለመጥፎ ስራቸው ንስሃ አልገቡም፤ ስለዚህ፣ በቁጣዬ ᵐእጎበኛቸዋለሁ፣ አዎን በኃይለኛው ቁጣዬ በክፋታቸውና በእርኩሰታቸው ምክንያት እጎበኛቸዋለሁ።

፪ አዎን፣ ለዚህ ትውልድ ወዮለት! እናም ጌታም አለኝ፡ እጅህን ዘርጋና እንዲህ ብለህ ተንብይ፡ ጌታ እንዲህ ይላል፣ እንዲህም ይሆናል፣ ይህ ትውልድ በጥፋቱ የተነሳ ወደ ᵐባርነት ይወሰዳል፣ ᵃጉንጨንም ይመታል፤ አዎን በሰዎች ይነዳልም ይገደላልም፣ እናም የሰማይ ጥንብ አንሳዎችና፣ ውሾች፣ አዎን፣ የዱር አራዊቶችም ᵐሥጋቸውን ይቀረማመቱታል።

፫ እናም እንዲህ ይሆናል፣ የንጉስ ኖህ ᵐህይወት ᵃእሳት ውስጥ እንደገባ ጨርቅ ይሆናል፤ እኔ ጌታ መሆኔን ያውቃልና።

፬ እናም እንዲህ ሆነ ይህን የኔፊን ህዝብ በታላቅ ስቃይ እመታዋለሁ፣ አዎን፣ በረሃብና ᵐበቸነፈር፤ እናም ቀኑን ሙሉ ᵃእንዲያለቅሱ አደርጋለሁ።

፭ አዎን፣ እናም በትከሻቸው ᵐሸክም እንዲሸከሙ አደርጋለሁ፣ እናም አንደበት እንደሌለው አህያም ይነዳሉ።

፳፬ *ሀ* ሚክ. ፫፡ ፬፣
ሞዛያ ፳፭፡ ፲፫።
፳፭ *ሀ* ኢሳ. ፭፡ ፲፫፣ ፶፱፡ ፪።
፳፯ *ሀ* ዘፀአ. ፭፡ ፪፣
ሞዛያ ፲፪፡ ፲፫።
፳፱ *ሀ* ሙሴ ፬፡ ፬።
ለ አልማ ፴፣ ፳፡
ኤተር ፲፭፡ ፲፣ ፲ሀ።
፲፪ ፭ *ሀ* ኢሳ. ፳፭፡ ፯።
፪ *ሀ* ሞዛያ ፲፭፡ ፳፭፣ ፳፡ ፳፭፣
፳፭፡ ፲፣–፲፭፣ ፳፣ ፡ ፳፭–፳፣።
ለ ሞዛያ ፳፭፡ ፣–፬።
፣ *ሀ* ሞዛያ ፲፪፡ ፲።
ለ ሞዛያ ፲፱፡ ፳።
፬ *ሀ* ት. እና ቃ. ፶፯፡ ፳፯።
ለ ሞዛያ ፳፭፡ ፱–፲።
፭ *ሀ* ሞዛያ ፳፭፡ ፣።

፮ እናም እንዲህ ይሆናል በረዶን በመ
ካከላቸው እልካለሁ፣ ይመታቸዋልም፤
እናም [ሀ]በምስራቅ ንፋስም ደግሞ ይመ
ታሉ፤ [ለ]ተምች ደግሞ ምድራቸውን ይወ
ራሉ፣ እህላቸውንም ይጨርሳሉ።

፯ እናም በታላቅ ቸነፈር ይመታሉ—
እናም ይህንን ሁሉ የማደርገው [ሀ]በክፋታ
ቸውና በእርኩሰታቸው የተነሳ ነው።

፰ እናም እንዲህ ይሆናል፣ ንስሃ ካልገቡ
በቀር ከምድር ገፅ [ሀ]አጠፋቸዋለሁ፤ ይሁን
እንጂ [ለ]ታሪካቸውን አስቀርተው ይሄዳሉ፣
እናም ምድሪቱን ለሚወርሱ ትውልድ አስ
ቀምጥላቸዋለሁ፤ አዎን፣ ይህንንም የማደ
ርገው የሌላው ሀገር የዚህን ህዝብ እርኩሰት
እንዲያውቀው ነው። እናም አቢናዲ በዚህ
ህዝብ ላይ ብዙ ነገሮችን ተንብዮአል።

፱ እናም እንዲህ ሆነ በእርሱ ተቆጥተው
ነበር፤ እናም ወሰዱትና በንጉሱ ፊትም አስ
ረው አቀረቡት፣ ለንጉሱም እንዲህ አሉት፥
እነሆ፣ ስለህዝብህ በክፉ የተነበየውን ሰው፣
እናም እግዚአብሔር እንደሚያጠፋቸው
የሚናገረውን በፊትህ አምጥተናል።

፲ እናም ደግሞ ህይወትህን በሚመለ
ከት ክፉን ነገር ተንብዮአል፤ እናም ህይ
ወትህ በሚነደው እሳት ውስጥ እንደሚሆ
ነው ጨርቅ እንደሚሆን ተናግሯል።

፲፩ እናም እንደገና፣ በአውሬዎች እንደ
ተጨፈለቀና በእግራቸውም እንደተረገጠ
አገዳ፤ የደረቅ ሜዳ አገዳ ትሆናለህ ሲል
ተናግሯል።

፲፪ እናም በድጋሚ፣ ሙሉ በሙሉ በሚ
ያብብበት ጊዜ ንፋሱም ከነፈሰ በምድሪቱ
ላይ እንደሚበተን እንደኮሸሸላ አበባ ትሆ
ናለህ ብሏል። ጌታም እንደተናገረ አስመ
ሰለ። እናም ንስሃ ካልገባህ፣ ይህ ሁሉ በአ
ንተ ላይ ይሆናል፣ ይህ የሆነውም በኃጢያ
ትህ የተነሳ ነው ሲል ተናግሯል።

፲፫ እናም አሁን፣ ንጉስ ሆይ፣ አንተ
ምን ያህል ክፉን ነገርን ሰርተሃል፣ ወይም
ህዝብህስ ምን ያህል ታላቅ ኃጢያትን
ፈፅሞአል፣ በእግዚአብሔርስ ዘንድ የም
ንኮነነው በዚህ ሰው የሚፈረድብን?

፲፬ እናም አሁን፣ ንጉስ ሆይ፣ እነሆ፣ እኛ
ጥፋተኞች አይደለንም፣ እናም አንተ ንጉስ
ሆይ ኃጢያትን አላደረግህም፤ ስለዚህ፣ ይህ
ሰው አንተን በሚመለከት ዋሽቷልና፣ በከ
ንቱ ተንብዮአል።

፲፭ እናም እነሆ፣ እኛ ጠንካሮች ነን፣ ወደ
ባርነትም አንመጣም፣ ወይም በጠላቶቻች
ንም በምርኮ አንወሰድም፤ አዎን፣ አንተ
በምድሪቱ በልፅገሃል እናም ደግሞ ትበለ
ፅጋለህ።

፲፮ እነሆ ሰውየውም ይህ ነው፣ እርሱን
በእጅህ አሳልፈን እንሰጥሀለን፤ መልካም
እንደመሰለህ በእርሱ ላይ አድርግ።

፲፯ እናም እንዲህ ሆነ ንጉስ ኖህ አቢናዲ
ወደ ወህኒ እንዲጣል አደረገ፤ እናም ከእ
ርሱ ጋር ምን ማድረግ እንዳለበት ምክር
ለማድረግ [ሀ]ካህናት ከእርሱ ጋር እራሳቸ
ውን በአንድነት እንዲሰበስቡ አዘዘ።

፲፰ እናም እንዲህ ሆነ ለንጉሱ እንዲህ
አሉት፥ እኛ እንድንጠይቀው ዘንድ ወደ
ዚህ አምጣው፤ እናም ከፊታቸው እንዲ
መጣም ንጉሱ አዘዘ።

፲፱ እናም ይቃረኑት ዘንድ፣ በዚህም
እርሱንም ለመክሰስ ምክንያት ያገኙ ዘንድ
መጠየቅ ጀመሩ፤ ነገር ግን በጉብዝና መለ
ሰላቸውና፣ ጥያቄአቸውን በሙሉ [ሀ]ተቋ
ቋማቸው፣ አዎን፣ እስከሚደንቃቸውም፤
ጥያቄአቸውን ሁሉ ተቋቋመ እናም በሁ
ሉም ቃላቸው ዝም አስኛቸው።

፳ እናም እንዲህ ሆነ ከእነርሱ መካከል
አንዱ እንዲህ አለው፥ አባቶቻችን ያስተ
ማሯቸው እናም እንዲህ የሚሉት እነዚህ
የተፃፉት ቃላት የሚሉት ምንድን ነው፤

፳፩ ሰላምን ያበሰረ፣ መልካም የሆነውን
መልካም የምስራች ወሬ ያበሰረ፣ ደህንነ
ትን ያወጀ፣ ለፅዮንም አምላካችሁ ነግሶ

፮ ሀ ኤር. ፲፰፡፲፯፣ ሞዛያ ፮፡ ፴፩።
ለ ዘፀአ. ፲፡ ፩–፲፪።

፯ ሀ ት. እና ቃ. ፫፡ ፲፰።
፰ ሀ አልማ ፵፭፡ ፱–፲ፀ።
ለ ሞር. ፰፡ ፲ፀ–፲፯።

፲፯ ሀ ሞዛያ ፲፩፡ ፲፩።
፲፱ ሀ ት. እና ቃ. ፲፡ ፭–፮።

አል! ያለው፣ መልካም የምስራች ይዞ የመ
ጣው በተራራው ላይ ያለው እግሮቹ ᵐእን
ዴት ያማሩ ናቸው፤
፳፪ ጠባቂዎቻቸሁ ጮክ ይላሉ፤ በአንድ
ነት ድምፅ ይዘምራሉ፤ ጌታ ፅዮንን በድጋሚ
ሲያመጣ ዐይን ለዐይን ይተያያሉና፤
፳፫ በደስታ በድንገት ውጡ፤ የፈራረ
ሳችሁ የኢየሩሳሌም ቦታዎች በአንድነት
ዘምሩ፤ ጌታ ህዝቡን አፅናንቷል፣ ኢየሩ
ሳሌምን አድኗልና።
፳፬ ጌታ ቅዱስ ᵐክንዶቹን በሀገሩ ዐይን ላይ
ገልጧል፣ እናም የአለም ዳርቻዎች ሁሉ
የአምላካችንን ማዳን ያያሉ?
፳፭ እናም አሁን አቢናዲ እንዲህ አላ
ቸው፡ እናንተ ᵐካህናት ናችሁን፣ እናም
ይህን ህዝብ ለማስተማርና የትንቢትን መን
ፈስ የምትረዱ እያስመሰላችሁ፣ እናም ግን
እነዚህን ነገሮች ምን ማለት እንደሆኑ ከእኔ
ለማወቅ ትፈልጋላችሁን?
፳፮ እናም እንዲህ እላችኋለሁ የጌታን
መንገድ ለምታጣምሙት ለእናንተ ወዮ
ላችሁ! እነዚህን ነገሮች የምትረዱ ከሆና
ችሁ አታስተምሯቸውምና፤ ስለዚህ የጌ
ታን መንገድ አጣምማችኋል።
፳፯ እናንተ ᵐለመረዳት ልባችሁን አላዘጋ
ጃችሁም፣ ስለዚህ፣ ብልህ አልነበራችሁም።
ስለዚህ፣ ለዚህ ህዝብ ምን ታስተምራላችሁ?
፳፰ እናም እነርሱ፣ የሙሴን ህግ እናስ
ተምራለን አሉ።
፳፱ እናም በድጋሚ እንዲህ አላቸው፡
የሙሴን ᵐህግ ካስተማራችሁ ለምን እናን
ተስ አልጠበቃችሁትም? ለምንስ ልባችሁን
በሀብት ላይ አደረጋችሁ? ለምንስ ᶮዝሙትን
ፈፀማችሁ፣ እንዲሁም ከጋለሞታዎች ጋር
ጉልበታችሁን አባከናችሁ፣ ስለዚህም ጌታ
በዚህ ህዝብ ላይ፣ አዎን እንዲያውም ታላቅ
ክፋት በዚህ ህዝብ ላይ እንድተነብይ እስኪ
ልከኝ፣ አዎን፣ እናም ይህን ህዝብ ኃጢያት
እንዲፈፅም አደረጋችሁ?
፴ እውነትን እንደምናገር አታውቁምን?
አዎን፣ እኔ እውነትን እንደምናገር ታው
ቃላችሁ፤ እናም በጌታ ፊት መንቀጥቀጥ
አለባችሁ።
፴፩ እናም እንዲህ ይሆናል በኃጢአታችሁ
የተነሳ ትመታላችሁ፣ ምክንያቱም የሙ
ሴን ህግ እናስተምራለን ብላችኋልና። እናም
ስለሙሴ ህግስ ምን ታውቃላችሁ? ᵐደህን
ነት በሙሴ ህግ አማካኝነት ይመጣልን? እና
ንተ ምን ትላላችሁ?
፴፪ እናም ደህንነት በሙሴ ህግ አማካኝ
ነት ይመጣል ብለው መለሱ።
፴፫ ነገር ግን አሁን አቢናዲ እንዲህ አላ
ቸው፡ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ብትጠ
ብቁ እንደምትድኑ አውቃለሁ፤ አዎን፣
ᵐበሲና ተራራ ጌታ እንዲህ ሲል ለሙሴ
የሰጠውን ህግ ብትጠብቁ፡
፴፬ ከግብፅ ምድር ያወጣኋችሁ፣ ከባር
ነት ቤት ᵐያወጣኋችሁ ᶮእኔ ጌታ አምላካ
ችሁ ነኝ።
፴፭ ከእኔ በቀር ᵐሌላ አምላክ አይኑራ
ችሁ።
፴፮ በላይ በሰማይ ካለው፣ በታች በምድር
ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ፣ የተቀረ
ፀውን ምስል ለእናንተ አታድርጉ።
፴፯ አሁን አቢናዲ እንዲህ አላቸው፡ ይህ
ንን ሁሉ አድርጋችኋልን? አላደረጋችሁም
እላችኋለሁ። እናም ይህ ህዝብ ይህንን ሁሉ
ነገር እንዲያደርግ ᵐአስተምራችኋልን? እኔ
አላደረጋችሁም እላችኋለሁ።

ምዕራፍ ፲፫

*አቢናዲ በመለኮታዊ ኃይል ተጠበቀ—አሥ
ርቱን ትዕዛዛት አስተማረ—ደህንነት በሙሴ*

፳፭ ᵐ ኢሳ. ፶፪፡፯–፲፣
ናሆ ፩፡ ፲፭።
፳፰ ᵐ ፩ ኔፊ ፳፪፡ ፲፩።
፳፭ ᵐ ሞዛያ ፲፩፡ ፩።
፳፯ ᵐ ቅ.መ.መ. ማስተዋል።
፳፱ ᵐ ቅ.መ.መ. የሙሴ ህግ።
ᶮ ቅ.መ.መ. ማመንዘር።
፴፩ ᵐ ሞዛያ ፫፡ ፲፭፣ ፲፫፡ ፳፯–፴፪፣
አልማ ፳፭፡ ፲፯።
፴፫ ᵐ ዘፀአ. ፲፱፡ ፱፣ ፲፯–፳፣
ሞዛያ ፲፫፡ ፭።
፴፬ ᵐ ዘፀአ. ፲፪፡ ፶፩፣
፩ ኔፊ ፲፯፡ ፶፣
ሞዛያ ፯፡ ፲፱።
ᶮ ዘፀአ. ፳፡ ፪–፬።
፴፭ ᵐ ሆሴ. ፲፫፡ ፬።
ቅ.መ.መ. ጣአት አምላኪ።
፴፯ ᵐ ሞዛያ ፲፫፡ ፳፭–፳፯።

ህግ ብቻ አይመጣም—እግዚአብሔር ራሱ የኃጢያት ክፍያ ያደርጋል፣ እናም ህዝቡን ያድናል። በ፪ሺ፯ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም አሁን ንጉሱ ይህንን ቃላት በሰማ ጊዜ፣ ለካህናቱ እንዲህ አላቸው፡ ይሄንን ሰው ውሰዱና ግደሉት፤ እብድ ስለሆነ ከእ ርሱስ ምን እናደርጋለን።

፪ እናም ተነሱና እጃቸውን ሊጭኑበት ሞከሩ፣ ነገር ግን ተቋቋማቸውና እንዲህ አላቸው፡

፫ አትንኩኝ፣ እጃችሁን በእኔ ላይ ብትጭ ኑብኝ እግዚአብሔር ይመታችኋል፤ ምክ ንያቱም ጌታ እንድሰጥ የላከኝን መልዕ ክት አልሰጠሁምና፤ ወይም እንድነግራ ችሁ [1]የጠየቃችሁኝንም አልነገርኳችሁም፤ ስለዚህ እግዚአብሔር በዚህ ጊዜ እንድጠ ፋም አይፈቅድም።

፬ ነገር ግን እግዚአብሔር ያዘዘኝን ትዕዛዝ መፈፀም አለብኝ፤ እናም እውነቱን ስለነ ገርኳችሁ ተቆጥታችሁኛል። እናም እን ደገና፣ የእግዚአብሔርን ቃል በመናገሬ እብድ ነው ብላችሁ ፈረዳችሁብኝ።

፭ አሁን እንዲህ ሆነ አቢናዲ እነዚህን ቃላት ከተናገረ በኋላ የንጉስ ኖህ ህዝብ የጌታ መንፈስ በእርሱ ላይ በመሆኑ እጃቸ ውን ሊጭኑበት አልደፈሩም፤ እናም ልክ ሙሴ ፊቱ በሲና ተራራ ከጌታ ጋር ሲነጋገር እንደበራው ፊቱ እጅግ [2]አበራ።

፮ እናም በእግዚአብሔር [3]ኃይልና በስል ጣን ተናገረ፤ እናም እንዲህ በማለት ንግ ግሩን ቀጠለ፡

፯ እኔን የመግደል ኃይል እንደሌላችሁ ተመልክታችኋል፣ ስለዚህ፣ መልዕክቴን እጨርሳለሁ። አዎን፣ እናም ኃጢአታችሁን በተመለከተ እውነቱን ስለነገርኳችሁ ልባ ችሁን [1]እንደሚሰነጥካችሁ አስተውላለሁ።

፰ አዎን፣ እናም ቃሌ በመገረምና በአድ ናቆትና በቁጣ ይሞላችኋል።

፱ ነገር ግን መልዕክቴን እጨርሳለሁ፤ የምድን እስከሆነ፣ እናም የትም መሄዴ ችግር አያመጣም።

፲ ነገር ግን ይህን ያህል እነግራችኋለሁ፣ በእኔ ላይ የምታደርጉትም ከዚህ በኋላ ስለ ሚመጡት ነገሮች [1]ዓይነትና ጥላ ይሆናሉ።

፲፩ እናም አሁን ቀሪውን የእግዚአብሔ ርን [1]ትዕዛዛት አነብላችኋለሁ፣ ምክንያቱም እንደምገምተው በልባችሁ ውስጥ አልተ ፃፉምና፤ በአብዛኛው የህይወታችሁ ጊዜም ክፋትን እንዳጠናችሁና እንደተማራችሁ እገምታለሁ።

፲፪ እናም አሁን፣ በላይ በሰማይ ካለው፣ ከምድር በታች፣ ወይም ከምድር በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ፣ የተቀረፀውን ምስል ለአንተ አታድርግ ያል ኩአችሁን ታስታውሳላችሁ።

፲፫ እናም በድጋሚ፣ ራሳችሁን ለእነርሱ አትስገዱላቸው፣ ወይም አታገልግሉአቸ ውም፤ በሚጠሉኝ በልጆች፣ በሦስተኛና አራተኛ ትውልዶች፣ ላይ የአባቶችን ጥፋት የምጎበኝ እኔ ጌታ አምላክህ ቀናተኛ አም ላክ ነኝና።

፲፬ እናም ለሚወዱኝና ትዕዛዛቴንም ለሚ ጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምህረትን የማሳይ ነኝ።

፲፭ የእግዚአብሔር አምላክህን ስም በከ ንቱ አትጥራ፣ እግዚአብሔር ስሙን በከ ንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነፃውምና።

፲፮ [1]የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ።

፲፯ በስድስቱ ቀን ስራ፣ ተግባርህን ሁሉ አድርግ፤

፲፰ ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር አምላክህ ሰንበት ነው፤ አንተ፣ ወንድ ልጅህም ሴት ልጅህም፣ ሎሌህም፣ ገረ ድህም፣ ከብትህም፣ በደጆችህ ውስጥ ያለ እንግዳ በእነርሱ ምንም ስራ አይሠራም፤

፲፱ [1]በስድስቱ ቀን ጌታ ምድርንና ሰማ

---

[1]፲፫ሀ ሞዛያ ፲፪፡፳–፳፬። [2]ሀ ዘፀአ. ፴፬፡፳፱–፴፭። [3]ሀ ቅ.መ.መ. ሀይል።

[1]ሀ ፩ ኔፊ ፲፯፡፪። [1]ሀ ሞዛያ ፲፯፡፲፫–፲፱፤ አልማ ፳፭፡፲።

[1]፲፩ ሀ ዘፀአ. ፳፡፩–፲፯። [1]፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. የሰንበት ቀን። [1]፲፱ ሀ ዘፍጥ. ፩፡፴፩።

ይን፣ እናም ባህርንና፣ በውስጡ ያሉትን ሁሉ ሰርቷልና፤ ስለሆነም ጌታ የሰንበትን ቀን ባረካትና ቀደሳት።

፳ ጌታ እግዚአብሔር በምድር ላይ የተ ሰጡህ ቀናትም ይረዝሙልህ ዘንድ እናትና አባትህን ᵐአክብር።

፳፩ ᵐአትግደል።

፳፪ ᵐአታመንዝር፣ ᵃአትስረቅ።

፳፫ በባልንጀራህ ላይ ᵐበሃሰት አትመስ ክር።

፳፬ የባልንጀራህን ቤት አትመኝ፣ የባልን ጀራህን ሚስት፣ ሎሌውንም፣ ገረዱንም፣ በሬውንም፣ አህያውንም፣ የባልንጀራህ የሆነውን ማንኛውንም ነገር ᵐአትመኝ።

፳፭ እናም እንዲህ ሆነ አቢናዲ ይህንን አባባሉን ከጨረሰ በኋላ እንዲህ ሲል ተና ገራቸው፥ እነዚህ ሰዎች የጌታን ትዕዛዛት ይጠብቁ ዘንድ እነዚህን ነገሮች ሁሉ እን ዲያደርጉ በእርግጥ አስተምራችኋቸዋ ልን?

፳፮ አይደለም እላችኋለሁ፤ ብታደርጉት ኖሮ፣ ጌታ ይህንን ህዝብ በተመለከተ መጥቼ መጥፎ እንድተነብይ አያደርገኝም ነበር።

፳፯ እናም አሁን ደህንነት በሙሴ ህግ ይመጣል ብላችኋል። ᵐየሙሴን ህግ መጠ በቅ አሁንም ጠቃሚ ነው እላችኋለሁ፤ ነገር ግን የሙሴን ህግ መጠበቁ ከእንግዲህ ጠቃሚ ᵃየማይሆንበት ጊዜ ይመጣል እላ ችኋለሁ።

፳፰ እናም ከዚህ በተጨማሪ፣ እንዲህ እላችኋለሁ ᵐደህንነት ᵃበህግ ብቻ አይመ ጣም፤ እናም ᵇኃጢያት ክፍያን ለዚህ ህዝብ ኃጢያትና ጥፋት እግዚአብሔር እራሱ ባያ ደርገው ኖሮ በሙሴም ህግ ቢሆን መወገድ በማይችሉበት ሁኔታ መጥፋት ነበረባቸው።

፳፱ እናም አሁን ለእስራኤል ልጆች ህጉ መሰጠቱ አስፈላጊ ነበር፤ አዎን ᵐጥብቁ ህግም እንኳን ቢሆን፣ ምክንያቱም እነ ርሱ አንገተ ደንዳና፣ ኃጢያትን ለማድ ረግ ᵃፈጣንና ጌታ አምላካቸውን ለማስታ ወስ የዘገዩ ነበሩ፤

፴ ስለዚህ ለእነርሱ የተሰጣቸው ᵐህግ ነበር፣ አዎን የስራና ᵃየስርዓት ህግ፣ ከቀን ቀን አጥብቀው የሚጠብቁት ህግ፤ እነርሱን በመጠበቅ እግዚአብሔርን እና ለእርሱ ያላ ቸውን ተግባር ᵇእንዲያስታውሱ።

፴፩ ነገር ግን እነሆ እንዲህ እላችኋለሁ፣ እነዚህ ነገሮች ሁሉ ወደፊት ሊመጡ ላሉት ᵐምሣሌዎች ነበሩ።

፴፪ እናም አሁን፣ ህጉን ተረድተውት ነበርን? አልተረዱም እላችኋለሁ፤ ሁሉም ህጉን አልተረዱትም፤ እናም ይህም የሆ ነው ልባቸውን በማጠጠራቸው ነው፤ በእ ግዚአብሔር ቤዛነት ካልሆነ ᵐበቀር ማንም ሰው መዳን አለመቻሉን አልተረዱምና።

፴፫ እነሆ፣ ሙሴ ስለመሲሁ መምጣት፣ እንዲሁም እግዚአብሔር ህዝቡን እንደሚ ቤዥ አልተነበየምን? አዎን፣ እናም ዓለም ከመፈጠሯ ጀምሮ ይተነብዩ የነበሩ ᵐሁሉም ነቢያት ከሞላ ጎደል ይህን በተመለከተ አል ተነበዩምን?

፴፬ ᵐእግዚአብሔር እራሱ በሰው ልጆች መካከል እንደሚመጣ፣ የሰዎችን አምሳል እንደሚወስድ፣ እናም በታላቅ ኃይሉ በም ድር ገፅ ፊት እንደሚሄድ አልተናገሩምን?

፴፭ አዎን፣ እናም ደግሞ የሙታንን

፳ ሀ ማር. ፯፡፲።
፳፩ ሀ ማቴ. ፭፡፳፩–፳፪፤
ት. እና ቃ. ፴፪፡፲፰።
ቅ.መ.መ. ግድያ።
፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. ማመንዘር።
ለ ቅ.መ.መ. መስረቅ።
፳፫ ሀ ምሳ. ፳፬፡፳፰።
ቅ.መ.መ. ሐሰት።
፳፬ ሀ ቅ.መ.መ. መመኘት።
፳፯ ሀ ቅ.መ.መ. የሙሴ ህግ።
ለ ፫ ኔፊ ፱፡፲፱–፳፣ ፲፭፡፱–፳።
፳፰ ሀ ገላ. ፪፡፲፮።
ቅ.መ.መ. ቤዛ፣ ማዳን፣
ቤዛነት፣
ደህንነት።
ለ ገላ. ፪፡፳፩፤
ሞዛያ ፫፡፲፱–፲፭፤
አልማ ፳፭፡፲፭–፲፯።
ሐ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ዋጋን
መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ።
፳፱ ሀ ኢያ. ፩፡፯–፰።
ለ አልማ ፴፯፡፰።
፴ ሀ ዘፀአ. ፳።
ለ ቅ.መ.መ. ስነስርዓቶች።
ሐ ያዕቆ. ፬፡፭።
፴፩ ሀ ሞዛያ ፲፯፡፲፱፤
አልማ ፳፭፡፲፭።
ቅ.መ.መ. ምሳሌዎች።
፴፪ ሀ ፪ ኔፊ ፳፭፡፳፫–፳፭።
፴፫ ሀ ፩ ኔፊ ፲፡፭፤
ያዕቆ. ፬፡፬፣ ፯፡፲፩።
፴፬ ሀ ሞዛያ ፯፡፳፯፣ ፲፭፡፩–፫።
ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣
አምላክ።

ᵐትንሳኤ እንደሚያስገኝ፣ እናም እራሱ እንደሚጨቆንና እንደሚሰቃይም አልተ ናገሩምን?

ምዕራፍ ፲፬

ኢሳይያስ ስለመሲሁ ተናገረ—የመሲሁ መዋረድና መሰቃየት ተገልፆአል—ነፍ ሱን ለኃጢያት መስዋዕት ሰጠ፣ እናም ለተላለፉት አማላጅ ሆነ—ኢሳይያስ ፶፫ን አነጻፅሩ። በ፲፯፹ ም.ዓ. ገደማ።

፩ አዎን፣ ኢሳይያስም እንኳን ይህን አላ ለምን፤ የእኛን ዜና ማን አምኗል፣ እናም የጌታስ ክንድ ለማን ተገልጧል?

፪ በፊቱ እንደቡቃያ ከደረቅም መሬት እንደስር አድጓል፣ መልክና ውበት የለ ውም፣ ባየነውም ጊዜ እንወደው ዘንድ ደም ግባት የለውም።

፫ በሰውም የተጠላና የተናቀ ነው፤ ህማ ምና ሀዘንን የሚያውቅ ሰው ነው፣ እናም ፊታችንንም ከእርሱ ሰወርን፤ የተጠላ ነበር፤ እኛም አላከበርነውም።

፬ በእውነት ᵐስቃያችንን ᵃተቀበለ፤ እናም ሀዘናችንን ተሸከመ፤ እኛ ግን እንደተቸገረ፣ በእግዚአብሔር እንደተቀሰፈና እንደተ መታ ቆጠርነው።

፭ ነገር ግን ᵐስለመተላለፋችን እርሱ ቆሰለ፤ ስለበደላችንም ደቀቀ፤ የሰላማችን ተግሳፅ በእርሱ ላይ ነበር፤ እናም በቁስሉ ᵃተፈወስን።

፮ እኛ ሁላችንም እንደ ᵐበጎች ተቅበዝብ ዘን ጠፋን፤ ከእኛ እያንዳንዱ ወደገዛ መን ገዱ አዘነበለ፤ እናም ጌታ የሁላችንንም በደል በእርሱ ላይ አኖረ።

፯ ተጨነቀ፤ እናም ተሰቃየ፣ ᵐአፉንም አልከፈተም ነበር፤ እንደበግ ለመታረድ ቀረበ፤ እናም በሸላቾቿ ፊት ዝም እንደ ምትል ᵃበግ አፉን አልከፈተም።

፰ ከወህኒና ከፍርድ ተወሰደ፤ እናም ስለ ትውልዱስ የሚያስተውልስ ማን ነው? እርሱ ከህያዋን ምድር ተወግዶአልና፤ ስለ ህዝቤም መተላለፍ ተመቷልና።

፱ እናም መቃብሩን ከክፉዎች ጋር አደ ረገ፤ እናም ሞቱን ᵐከባለጠጋዎች ጋር፤ ምንም ᵃክፉ ነገር አላደረገምና፤ በአንደ በቱም ተንኮል አልተገኘበትም።

፲ ይሁን እንጂ ጌታ እርሱን ማቁሰል አስ ደሰተው፤ በሃዘን ውስጥ ጨመረው፤ ነፍሱን ስለኃጢያት መስዋዕት ካደረገ በኋላ ᵐዘሩን ያያል፣ እድሜውን ያረዝማል፣ እናም የጌታ ፈቃድ በእጁ ውጤታማ ይሆናል።

፲፩ የነፍሱን ስቃይ ይመለከታል፣ እናም ደስ ይለዋል፤ ፃድቁ ባሪያዬም በእውቀቱ ብዙዎችን ያጸድቃል፤ ኃጢአታቸውንም ᵐይሸከማልና።

፲፪ ስለዚህ ከኃያላን ጋር ትልቁን አካፍ ለዋለሁ፤ እናም ከጠንካሮች ጋር ምርኮን ይከፋፈላል፤ ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቷ ልና፤ ህጉን ከተላለፉት ጋር ተቆጥሯልም፣ እናም የብዙዎችን ኃጢያት ተሸከመ፤ ስለ አመፀኞችም ᵐማለደ።

ምዕራፍ ፲፭

ክርስቶስ አባትም ልጅም እንዴት እንደ ሆነ—እርሱ ያማልዳል እናም የህዝቡን አመፅ ይሸከማል—እነርሱ እና ሁሉም ቅዱሳን ነቢያት ዘሮቹ ናቸው—ትንሳ ኤን ያመጣል—ህፃናት ዘለዓለማዊ ህይ ወት ይኖራቸዋል። በ፲፯፹ ም.ዓ. ገደማ።

፴፭ ሀ ኢሳ. ፳፭፤ ፲፱፣
፪ ኔፊ ፪፡ ፳።
፲፬ ፩ሀ ማቴ. ፳፡ ፲፯።
ለ አልማ ፯፡ ፲፩–፲፪።
፭ሀ ሞዛያ ፲፭፡ ፱፣
አልማ ፲፩፡ ፵።
ለ ፩ ጴጥ. ፪፡ ፳፬–፳፭።
፯ሀ ማቴ. ፱፡ ፴፯፣
፪ ኔፊ ፳፰፡ ፲፡
አልማ ፭፡ ፴፯።
፯ሀ ማር. ፲፭፡ ፫።
ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ።
ለ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር
በግ፣
ፋሲካ።
፱ሀ ማቴ. ፳፯፡ ፶፯–፳፡
ማር. ፲፭፡ ፳፯፣ ፴፫–፴፯።
ቅ.መ.መ. የእርማትያስ
ዮሴፍ።
ለ ዮሐ. ፲፱፡ ፩።
፲ ሀ ሞዛያ ፲፭፡ ፲–፲፫።
፲፩ ሀ ዘሌዋ. ፲፯፡ ፳፩–፳፪፣
፩ ጴጥ. ፫፡ ፲፰፣
ት. እና ቃ. ፲፱፡ ፲፯–፲፱።
፲፪ ሀ ፪ ኔፊ ፪፡ ፱፣
ሞዛያ ፲፭፡ ፳፣
ሞሮኒ ፯፡ ፳፯–፳፰።

፩ እናም አሁን፣ አቢናዲ እንዲህ አላ
ቸው፡ ᵇእግዚአብሔር ራሱ በሰው ልጆች
መካከል እንደሚወርድና፣ ህዝቡንም ᵃእን
ደሚያድን እንድትረዱ እፈልጋለሁ።
፪ እናም በስጋ ᵇበመኖሩም የተነሳ የእግ
ዚአብሔር ልጅ ተብሎ ይጠራል፣ እናም
ᶜሥጋውን ᵃለአብ ፈቃድ በማስገዛቱ አብም፣
ወልድም ነው—
፫ በእግዚአብሔር ኃይል ᵇየተፀነሰ ᵃስለሆ
ነም አብ ነው፤ ስጋን ለብሷልና ወልድ ነው፣
ስለዚህ አብም ወልድም ነው—
፬ እናም ᵇአንድ አምላክ፣ አዎን፣ እውነ
ተኛ የሰማይና የምድር ᵃዘለዓለማዊ ᶜአባት
ናቸው።
፭ እናም ስጋው ለመንፈስ ወይንም ወል
ድም ለአብ በመገዛቱ፣ አንድ አምላክ በመ
ሆን፣ መከራን ᵇበመሰቃየቱና፣ ለፈተናም
ራሱን ባለመስጠቱ፤ ነገር ግን እንዲሳለቁበ
ትና፣ ᵃእንዲገረፍ፣ እንዲሁም በህዝቡ እን
ዲጣልና ᶜእንዲወገዝ ራሱን አሳልፎ ሰጠ።
፮ እናም ከዚህ ሁሉ በኋላ፣ በሰው ልጆች
መካከል ብዙ ኃያል ድንቅ ሥራዎችን ከሰራ
በኋላ ይመራል፣ አዎን፣ ኢሳይያስ ᵇእንዳ
ለው ሁሉ፣ በጉም በሸላቾቹ ፊት ዝም እን
ዳለው፣ እንዲሁም ᵃአፉን አልከፈተም።
፯ አዎን፣ እንደዚያ ቢሆንም እርሱ
ይነዳል፣ ᵇይሰቀላል እናም ይገደላል፣ ᵃየወ
ልድም ፈቃድ በአብ ፈቃድ ተሸፍኖ፣ ስጋ
ውም ቢሆን ሞትን እንዲቀምስ ይደረጋል።
፰ እና በሞት ላይ ᵇድልን በማግኘት፣
ለሰው ልጆች ᵃእንዲማልድ ለወልድ ኃይ
ልን በመስጠት፣ እንደዚህም እግዚአብሔር
ᶜየሞትን እስር ይበጥሳል፤
፱ ወደሰማይ በማረጉ፣ ለሰው ልጆች አን
ጀቱ በምህረት በመሞላቱ፣ በእነርሱና በፍ
ርድ መካከል በመቆም ለሰዎች ልጆች በርህ
ራሄ ይሞላል፣ የሞትን እስር በመበጣጠስ፣
ᵇበራሱም ላይ ክፋታቸውንና መተላለፋቸ
ውን በማድረግ፣ እነርሱን በማዳን፣ እናም
የፍትህን ፍላጎት ᵃአሟልቷል።
፲ እናም አሁን እላችኋለሁ፣ ትውልዱን
የሚያውጅ ማን ነው? እነሆ፣ እላችኋለሁ፣
ነፍሱ ለኃጢያት መስዋዕት ሲሆን ᵇዘሩን
ያያል። እናም አሁን ምን ትላላችሁ? እናም
ዘሩስ ማን ይሆናል?
፲፩ እነሆ እላችኋለሁ፣ ማንም ᵇየነቢያ
ቱን ቃላት የሰማ፣ አዎን የክርስቶስን መም
ጣት በተመለከተ የተነበዩትን ቅዱሳን ነቢ
ያት ሁሉ—እላችኋለሁ፣ ቃላቸውን የሰሙ
ሁሉ፣ እናም ጌታ ህዝቡን ማዳኑን ያመኑና፣
ለኃጢአታቸው ስርየት ያንን ቀን የሚጠ
ብቁ፣ እላችኋለሁ፣ እነዚህ የእርሱ ዘር
ናቸው፣ ወይም ᵃየእግዚአብሔርን መንግ
ስት ወራሾች ናቸው።

፲፭ ፩ ᵇ ፩ ጢሞ. ፫፡፲፮፤
ሞዛያ ፲፫፡ ፴፫–፴፭።
ᶜ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ
ክርስቶስ።
ᵃ ቅ.መ.መ. ቤዛ፣ ማዳን፣
ቤዛነት።
፪ ᵇ ሞዛያ ፫፡ ፭፤ ፯፡ ፳፯፤
አልማ ፯፡ ፱–፲፫።
ᵃ ኢሳ. ፳፭፡ ፳፤
ዮሐ. ፲፡ ፴፤ ፲፩፡ ፳–፲፤
ሞዛያ ፭፡ ፯፤
አልማ ፲፩፡ ፴፳–፴፱፤
ኤተር ፫፡ ፲፩።
፫ ᵇ ሉቃ. ፩፡ ፴፩–፴፫፣
ሞዛያ ፫፡ ፳–፱፤
አልማ ፯፡ ፲፣
፫ ኔፊ ፩፡ ፲፩።
ᵃ ት. እና ቃ. ፯፣፡ ፭።
፬ ᵇ ዘዳግ. ፮፡ ፬፤
ዮሐ. ፲፯፡ ፳–፳፣፡
ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣
አምላክ።
ᵃ አልማ ፲፩፡ ፴፱።
ᶜ ሞዛያ ፣፡ ፳፤
ሔለ. ፲፩፡ ፲፪፤
፣ ኔፊ ፱፡ ፲፩፤
ኤተር ፭፡ ፯።
፭ ᵇ ሉቃ. ፭፡ ፪፤
ዕብ. ፭፡ ፲፩–፲፭።
ᵃ ዮሐ. ፲፱፡ ፩።
ᶜ ማር. ፳፡ ፴፩፣
ሉቃ. ፲፯፡ ፳፭።
፮ ᵇ ኢሳ. ፶፣፡ ፯።
ᵃ ሉቃ. ፳፣፡ ፱፤
ዮሐ. ፲፱፡ ፱፤
ሞዛያ ፲፡ ፯።
፯ ᵇ ቅ.መ.መ. መሰቀል።
ᵃ ሉቃ. ፳፪፡ ፶፪፤
ዮሐ. ፮፡ ፴፳፤
፣ ኔፊ ፲፩፡ ፲፩።
፰ ᵇ ሆሴ. ፲፣፡ ፲፡
፩ ቆሮ. ፲፭፡ ፶፭–፶፯።
ᵃ ፪ ኔፊ ፪፡ ፱።
ᶜ ሞዛያ ፲፯፡ ፯፤
አልማ ፳፪፡ ፲፡።
፱ ᵇ ኢሳ. ፶፣፡ ፲።
ᵃ ሞዛያ ፭፡ ፯፤ ፳፯፤ ፳፭፤
ሞሮኒ ፯፡ ፲፱።
፲፩ ᵇ ት. እና ቃ. ፹፡ ፴፯–፴፰።
ᵃ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር
መንግስት ወይም መንግስተ
ሰማያት፣
ደህንነት።

፲፪ ኃጢአታቸውን ᐟየተሸከመላቸው እነ ዚህ ናቸው፤ ከመተላለፋቸው እንዲያድ ናቸው እርሱ የሞተላቸው እነርሱ ናቸው። እናም አሁን የእርሱ ዘሮች አይደሉምን?

፲፫ አዎን፣ እናም ለትንቢት አፉን የከፈተ እያንዳንዱ፣ በመተላለፍ ያልወደቀ፣ ማለ ትም ዓለም ከመፈጠሩ ጀምሮ የነበሩ ቅዱ ሳን ነቢያት ሁሉ አይደሉምን? እነርሱ ዘሮቹ ናቸው እላችኋለሁ።

፲፬ እናም ሰላምን ᐟየተናገሩት፣ መልካ ሙን የምስራች ዜና ያመጡት፣ ደህንነ ትን የተናገሩት፣ እናም ለፅዮንም አምላ ክሽ ነግሷል! ያሉት እነኚህ ናቸው።

፲፭ እናም አቤቱ እግራቸው በተራራው ላይ ምን ያህል ያማረ ነው!

፲፮ እናም እንደገና፣ ሰላምን በተራራው ላይ የሚያውጁ እግራቸው እንዴት ያማረ ነው?

፲፯ እናም እንደገና፣ አዎን፣ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እስከዘለዓለም በተራራው ላይ ሰላ ምን የሚያውጁት እግራቸው እንዴት ያማረ ነው!

፲፰ እናም እነሆ፣ እንዲህ እላችኋለሁ፣ ይህ ብቻም አይደለም። ᐟየሰላም መስራቹ የምስራች ወሬን ያመጣው፣ ህዝቡን ያዳነው አዎን፣ ያውም ጌታ ቢሆን እንኳን፣ አዎን፣ ለህዝቡ ደህንነትን የሰጠው፣ ᐞእግሮቹ በተ ራራው ላይ ምን ያህል ያማሩ ናቸው።

፲፱ ከዓለም ᐟመፈጠር ጀምሮ የተዘጋጀው ለህዝቡ ያደረገው ቤዛነት ባይሆን ኖሮ፣ ይህ ባይሆን ኖሮ የሰው ዘር በሙሉ ᐞመጥፋት ነበረባቸው እላችኋለሁ።

፳ ነገር ግን እነሆ፣ የሞት እስር ይበጠሳል፣ እናም ወልድም ይነግሳል፣ በሞት ላይ ስልጣን ይኖረዋልም፣ ስለዚህ፣ የሞትን ትንሣኤ ያመጣል።

፳፩ እናም ትንሳኤ፣ እንዲያውም ᐟየመ ጀመሪያው ትንሣኤ፣ አዎን፣ ትንሣኤውም እንኳን ለነበሩትና፣ አሁን ላሉት፣ እናም ወደፊት ለሚኖሩት እስከ ክርስቶስ ትንሳ ኤም ድረስ እንኳን ይመጣል፤ እንዲህም ተብሎ ነው ይጠራልና።

፳፪ እናም አሁን፣ ሁሉም ነቢያትና፣ በቃላቸው ያመኑት ሁሉ፣ ወይም የእግዚ አብሔርን ትዕዛዛት የሚጠብቁ ሁሉ፣ በመ ጀመሪያው ትንሳኤ ይነሳሉ፣ ስለዚህ፣ የመ ጀመሪያው ትንሣኤ ናቸው።

፳፫ ካዳናቸው ከእግዚአብሔር ጋር ᐟለመ ኖር ይነሳሉ፤ እንደዚህም የሞትን እስር ᐞበበጠሰው፣ በክርስቶስ በኩል ዘለዓለማዊ ህይወት ያገኛሉ።

፳፬ እናም እነዚህ በመጀመሪያው ትንሣኤ ቦታ ያላቸው ናቸው፤ እነዚህም ባለማወቃ ቸው፣ ᐟደህንነት ሳይታወጅላቸው፣ ክር ስቶስ ከመምጣቱ በፊት የሞቱት ናቸው። እናም ጌታ የእነዚህ መታደስን ያመጣል፤ በመጀመሪያው ትንሣኤ ቦታ፣ ወይም በጌታ በመዳን ዘለዓለማዊ ህይወት ይኖራ ቸዋልም።

፳፭ እናም ትናንሽ ᐟልጆች ዘለዓለማዊ ህይወት ይኖራቸዋል።

፳፮ ነገር ግን እነሆ፣ እናም በእግዚአብሔር ፊት ᐟፍሩና ተንቀጥቀጡ፣ መንቀጥቀጥ ይገ ባችኋልና፣ ጌታም በእርሱ ላይ ᐞያመፀው ንና በኃጢያት ᐝየሞተውን አያድንምና፤ አዎን፣ እንዲሁም ዓለም ከተፈጠረች ጀምሮ በኃጢአታቸው የሞቱትም፣ ወደው በእግዚአብሔር ላይ ያመፁትም፣ የእግዚ

፲፪ ሀ ሞዛያ ፲፬፡፲፪፤
አልማ ፮፡፲፫፤ ፲፭፡ ፴–፴፩።
፲፬ ሀ ኢሳ. ፶፪፡ ፯፤
ሮሜ ፣፡ ፲፭፤
፩ ኔፊ ፲፫፡ ፴፯፤
ሞዛያ ፲፪፡ ፳፭–፳፱።
ቅ.መ.መ. የሚስዮን ስራ።
፲፭ ሀ ዮሐ. ፲፯፡ ፴፫።
ቅ.መ.መ. ሰላም።
ለ ፫ ኔፊ ፳፡ ፴፣
ት. እና ቃ. ፲፳፳፡ ፲፱።
፲፱ ሀ ሞዛያ ፱፡ ፯።
ለ ፪ ኔፊ ፱፡ ፯–፲፫።
፳፩ ሀ አልማ ፴፡ ፲፯–፳፩።
፳፫ ሀ መዝ. ፳፱፡ ፫–፱፤
፩ ኔፊ ፲፭፡ ፴፫–፴፯፤
ት. እና ቃ. ፫፯፡ ፱–፫።
ለ ቅ.መ.መ. ስጋዊ ሞት።
፳፱ ሀ ፪ ኔፊ ፱፡ ፳፭–፳፯፤
ት. እና ቃ. ፲፴፯፡ ፯።
፳፭ ሀ ት. እና ቃ. ፳፱፡ ፴፯፤
፲፴፯፡ ፲።
ቅ.መ.መ. ደህንነት—የልጆች ደህንነት።
፳፯ ሀ ዘዳግ. ፭፡ ፳፱፤
ያዕቆ. ፯፡ ፱።
ለ ፩ ኔፊ ፪፡ ፳፭–፳፱።
ሐ ሕዝ. ፲፳፡ ፳፯፤
፩ ኔፊ ፲፫፡ ፴፪–፴፫፤
ሞሮኒ ፣፡ ፳፯።

አብሔርን ትዕዛዛት የሚያውቁ እናም የማ
ይጠብቁትም ሁሉ፣ በመጀመሪያው ትን
ሳኤ ቦታ "ያልኖራቸው "እነዚህ ናቸው።

፳፯ ስለዚህ እናንተስ መንቀጥቀጥ አይገባ
ችሁምን? ደህንነት እንደነዚህ ላሉት ለማ
ናቸውም አይመጣም፣ ጌታ እንደዚህ ያሉ
ትን ማናቸውንም አያድንምና፤ አዎን፣
ጌታ እንዲህ አይነቱን ሊያድን አይቻለው
ምና፣ እራሱን ሊክድ አይችልምና፣ "ፍትህ
በሰው ላይ ቅጣት ለመስጠት መብት ሲኖ
ራት መካድ አይችልምና።

፳፰ እናም አሁን እንዲህ እላችኋለሁ፣
የጌታ ደህንነት ለሁሉም ሀገር፣ ነገድ፣ ቋን
ቋና ህዝብ "የሚታወጅበት ጊዜ ይመጣል።

፳፱ አዎን፣ ጌታ፣ "ጠባቂዎችህ ድምፃች
ውን ከፍ ያደርጋሉ፣ በአንድነትም ይዘም
ራሉ፤ ጌታ ፅዮንን በድጋሚ ሲያመጣ ዐይን
ለዐይን ይተያያሉና።

፴ በደስታ በድንገት ውጡ፤ የፈራረሳችሁ
የኢየሩሳሌም ቦታዎች በአንድነት ዘምሩ፤
ጌታ ህዝቡን አፅናንቷል፣ ኢየሩሳሌምን
አድኗልና።

፴፩ ጌታ ቅዱስ ክንዱን በሁሉ ሀገሮች
ዐይን ላይ ገልጧል፤ እናም የአለም ዳርቻ
ዎች ሁሉ የአምላካችንን ማዳን ያያሉ።

ምዕራፍ ፲፮

*እግዚአብሔር ሰዎችን ከጥፋትና ከው
ድቀት ሁኔታቸው ያድናል—በስጋ ያሉ
ቤዛነት እንደሌለ ሆነው ይቀራሉ—ክርስ
ቶስ መጨረሻ የሌለው ህይወትን ወይንም
መጨረሻ የሌለው ኩነኔ ትንሳኤን አመ
ጣው። በ፪ሟ፯ ም.ዓ. ገደማ።*

፩ እናም አሁን እንዲህ ሆነ፣ አቢናዲ እነ
ዚህን ቃላት ከተናገረ በኋላ ክንዱን ዘረጋና
አለ፥ ሁሉም የጌታን "ደህንነት የሚያዩበት
ቀን ይመጣል፤ ሁሉም ሀገር፣ ነገድ፣ ቋን
ቋና ህዝብ ዐይን ለዐይን ይተያያሉ እናም
በእግዚአብሔር ፊት ፍርዱ ትክክል እን
ደሆነ "ይናዘዛሉ።

፪ እና ከእዚያም ኃጢአተኞች "ይጣላሉ፣
እናም ዋይ እያሉ "የሚያለቅሱበትና በት
ካዜ የሚጮሁበት፣ እናም ጥርሳቸውን የሚ
ፋጩበት ምክንያት ይኖራቸዋል፣ ይህም
የሚሆነው የጌታን ድምፅ ስለማያዳምጡ
ነው፤ ስለዚህ ጌታ አያድናቸውም።

፫ "ስጋዊና አጋንንታዊ ናቸው፣ እናም
"ዲያብሎስ፣ አዎን፣ እንዲሁም ያ የቀ
ደመው እባብ እንዲያውም የመጀመሪያ
ወላጆቻችንን ሓያሳተው፤ "የውድቀታ
ቸው መንስኤ የሆነውን፣ ለሰው ዘር በሙሉ
ስጋዊነት፣ ስሜታዊነት፣ ዲያብሎሳዊነት፣
መጥፎን ከጥሩ ለይተው "በማወቅ ራሳቸ
ውን ለዲያብሎስ የሚያስገዙበት ምክንያት
የሆነው በእነርሱ ላይ ኃይል አለውና።

፬ የሰው ዘር ሁሉ "ጠፍቷል፣ እናም
እነሆ፣ እግዚአብሔር ህዝቡን ከጠፋበትና
ከውድቀት ባያድነው ኖሮ እስከመጨረሻው
በጠፋ ነበር።

፭ ነገር ግን አስታውሱ "በስጋዊ ተፈጥ
ሮው የቆየ፣ እናም በኃጢያትና በእግዚአ
ብሔር እያመፀ የተጓዘ፣ ወድቆ ይቀራል
እናም ዲያብሎስ ሙሉ ስልጣን በእርሱ
ላይ ይኖረዋል። ስለዚህ ለእግዚአብሔር
ጠላት ሆኖ፣ እርሱ "ቤዛነት እንዳልተደረ
ገለት ይሆናል፣ እናም ደግሞ ዲያብሎስም
የእግዚአብሔር ጠላት ነው።

፳፯ መ ት. እና ቃ. ፫፯፡ ፲ሸ–
፲ሸ፯።
ሠ አልማ ፵፡ ፲፱።
፳፯ ሀ አልማ ፴፪፡ ፲፭–፲፯፤
፵፪፡ ፭።
፳፰ ሀ ቅ.መ.መ. የሚስዮን ስራ።
፳፱ ሀ ቅ.መ.መ. መጠበቅ፣
ጠባቂ።
፲፯ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. ደህንነት።
ለ ሞዛያ ፳፯፡ ፴፩።
፪ ሀ ት. እና ቃ. ፳፫፡ ፶ሸ–፶፩።
ለ ማቴ. ፲ሸ፡ ፶፩–፶፪፤
ሉቃ. ፲ሸ፡ ፳፳፤
አልማ ፵፡ ፲ሸ።
ሸ ሀ ገላ. ፭፡ ፲፯–፳፭፤
ሞዛያ ሸ፡ ፲፱።
ቅ.መ.መ. ፍጥረታዊ ሰው።
ለ ፪ ኔፊ ፱፡ ፳–፱።
ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
ሐ ዘፍጥ. ሸ፡ ፩–፲ሸ፤
ሙሴ ፩፡ ፭–፲፱።
መ ቅ.መ.መ. የአዳም እና
የሔዋን ውድቀት።
ሠ ፪ ኔፊ ፪፡ ፲፯–፲፰፡ ፳፪–፳፯።
፩ ሀ አልማ ፶፪፡ ፯–፲፩።
፭ ሀ አልማ ፶፩፡ ፲፩።
ቅ.መ.መ. ስጋዊ።
ለ ቅ.መ.መ. ቤዛ፣ ማዳን፣
ቤዛነት።

፮ እናም፣ ስለነገሮች መምጣት ᵐእንደ መጡ በመናገር፣ እንግዲህ ክርስቶስ ወደ ዓለም ባይመጣ ኖሮ ቤዛ ሊሆን አይችልም ነበር።

፯ እናም ክርስቶስ ከሞት ባይነሳ ኖሮ፣ ወይም መቃብርም ድል እንዳይኖረውና ሞትም ᵐመውጊያ እንዳይኖረው፣ የሞትን እስር ባይበጣጥስ ኖሮ፣ ትንሣኤም ሊኖር አይችልም ነበር።

፰ ነገር ግን ᵐትንሳኤ አለ፤ ስለዚህ ሞት ድል አይኖረውም፤ እናም ᵃየሞት መውጊያ በክርስቶስ ተውጧል።

፱ እርሱ የዓለም ᵐብርሃንና ህይወት ነው፤ አዎን፣ መጨረሻ የሌለው፣ ሊጨልም የማ ይችል ብርሃን፤ አዎን እናም ደግሞ መጨ ረሻ የሌለው ህይወት፣ እናም ከእንግዲህ ሞት ሊሆን የማይችልበት።

፲ እንዲሁም ይህ የሚሞተው ᵐየማይሞተ ውን ይለብሳል፣ እናም ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ይለብሳል፣ እናም መጥ ፎም ይሁን መልካም እንደስራቸው መሰ ረት ᵃእንዲፈረድባቸው በእግዚአብሔር የፍርድ ወንበር ፊት ᵇይቆማሉ—

፲፩ መልካም ከሆኑ ᵐመጨረሻ ለሌለው ህይወትና ደስታ ትንሳኤ፤ እናም መጥፎ ከሆኑ፣ ኩነኔ ወደሆነው የእርሱ ላደረጋቸው ለዲያብሎስ በመሰጠት ᵃመጨረሻ ለሌለው የኩነኔ ትንሳኤ—

፲፪ እና በስጋዊ ፍቃዳቸውና ፍላጎታ ቸው መሰረት በመሄዳቸው፣ እናም ᵐየም ህረት ክንዶች ወደ እነርሱ ተዘርግተው ሳለ፣ ጌታን በጭራሽ ባለመጥራታቸው፤ የምህረት ክንዶች ወደ እነርሱ ተዘርግተ ዋልና፣ እነርሱም አልተቀበሉትም፤ ለጥ ፋታቸው ማስጠንቀቂያ ቢሰጣቸውም እነ ርሱ ግን ከእነዚህ አልሸሹም፤ እናም ንስሃ እንዲገቡ ታዘው ነበር ነገር ግን ንስሃ አል ገቡም።

፲፫ እናም አሁን፣ ልትንቀጠቀጡና፣ ለኃ ጢአታችሁ ንስሃ ልትገቡ አይገባችሁምን፤ እናም በክርስቶስ ብቻ ልትድኑ እንደምት ችሉ አታስታውሱምን?

፲፬ ስለዚህ፣ ᵐየሙሴን ህግ የምታስተምሩ ከሆነ፣ ደግሞ የሚመጣው ነገር ጥላ እንደ ሆነ አስተምሩ—

፲፭ ቤዛነት ᵐዘለዓለማዊ አባት በሆነው በጌታ በክርስቶስ እንደሚመጣ አስተምሯ ችው። አሜን።

ምዕራፍ ፲፯

አልማ የአቢናዲን ቃል አመነ እናም ፃፈ—አቢናዲ በእሳት ተቃጥሎ ሞተ—አቢናዲ በገዳዮቹ ላይ በሽታንና በእሳት ሞትን ተነ በየ። በ፲፯፻፳ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም አሁን እንዲህ ሆነ አቢናዲ ይህን ንግግሩን ሲጨርስ፣ ንጉሱ ᵐካህናት እንዲ ወስዱትና እንዲገድሉት አዘዘ።

፪ ነገር ግን ከእነርሱ መካከል ᵐአልማ የሚ ባል ሰው ነበር፤ እርሱም ደግሞ የኔፊ ትው ልድ ነበር። እርሱም ወጣት ነበር፣ እናም አቢናዲ በተናገራቸው ቃላት ᵃያምን ነበር፣ አቢናዲ ስለጥፋታቸው በእነርሱ ላይ ስለመ ሰከረው ያውቅ ነበርና፤ ስለዚህ ንጉሱ በአ ቢናዲ እንዳይቆጣ፣ ነገር ግን በሰላም እን ዲሄድ ለመነው።

፫ ነገር ግን ንጉሱ ይበልጥ ተቆጣ፤ እናም አልማ ከመካከላቸው ውጥቶ እንዲጣል

፮ *ሀ* ሞዛያ ፫፡ ፲፫።
፯ *ሀ* ሆሴ. ፲፫፡ ፲፬፤ ሞዛያ ፲፭፡ ፳፣ ፳፡ *ለ* ኢሳ. ፳፭፡ ፳፤ ፩ ቆሮ. ፲፭፡ ፶፬–፶፭፤ ሞር. ፯፡ ፭።
፱ *ሀ* ት.እና ቃ. ፹፰፡ ፭–፲፫። ቅ.መ.መ. ብርሀን፣ የክርስቶስ ብርሀን። ፲ *ሀ* አልማ ፵፡ ፪። ቅ.መ.መ. የማይሞት፣ አለሟችነት። *ለ* አልማ ፵፩፡ ፫–፮። *ሐ* ቅ.መ.መ. ፍርድ፣ የመጨረሻው። ፲፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. የዘለዓለም ህይወት። *ለ* ቅ.መ.መ. ኩነኔ። ፲፪ *ሀ* ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት። ፲፬ *ሀ* ቅ.መ.መ. የሙሴ ህግ። ፲፭ *ሀ* ሞዛያ ፫፡ ፳፣ ፭፡ ፮፤ ኤተር ፫፡ ፲፬። ፲፯ ፩ *ሀ* ሞዛያ ፲፩፡ ፩፣ ፭–፮። ፪ *ሀ* ሞዛያ ፳፫፡ ፮፣ ፱–፲። ቅ.መ.መ. ሽማግሌው አልማ። *ለ* ሞዛያ ፳፮፡ ፲፭።

አደረገ፣ እናም እርሱን ይገድሉት ዘንድ አገልጋዮችን ላከ።

፬ ነገር ግን ከፊታቸው ሸሸ፣ እናም እን ዳያገኙት ተደበቀ። እናም ለብዙ ቀናት ተሰውሮ አቢናዲ የተናገረውን ቃላት ሁሉ [ሀ]ፃፈ።

፭ እናም እንዲህ ሆነ ንጉሱ ጠባቂዎቹ አቢናዲን እንዲከቡትና እንዲወስዱት አደረገ፤ እናም አሰሩትና ወደ ወህኒ ቤት ጣሉት።

፮ እናም ከሶስት ቀናት በኋላ ከካህናቱ ጋር በመመካከር፣ በድጋሚ በፊቱ እንዲቀርብ አደረገ።

፯ እናም እንዲህ አለው፥ አቢናዲ፣ በአ ንተ ላይ ወንጀል አግኝተናልና ለሞት ብቁ ነህ።

፰ አንተ [ሀ]እግዚአብሔር ራሱ በሰው ልጆች መካከል ይመጣል ብለሃልና፤ እናም አሁን፣ በዚህ የተነሳ እኔንና ህዝቤን በተመ ለከተ የተናገርከውን መጥፎ ቃላት ካላስተ ባባልክ ትገደላለህ።

፱ አሁን አቢናዲም አለው፥ እልሀለሁ፣ ይህንን ህዝብ በተመለከተ የተናገርኩት ቃላት አላስተባብልም፣ እውነት ናቸውና፣ እናም እውነተኛነቱን ታውቁ ዘንድ በእና ንተ እጅ እንድወድቅ ለራሴ ፈቅጃለሁ።

፲ አዎን፣ እናም እስከሞቴም ድረስ እሰ ቃያለሁ፣ ቃሌንም አላስተባብልም፣ እነ ርሱም በእናንተ ላይ እንደምስክርነት ይቆ ማሉ። እናም እኔን የምትገድሉኝ ከሆነ [ሀ]ንፁህ ደም አፍሳችኋልና፤ ይህም በመ ጨረሻው ቀን ደግሞ በእናንተ ላይ እንደ ምስክር ይቆማል።

፲፩ እናም አሁን ንጉስ ኖህ እርሱን ሊለ ቀው ነበር፣ ምክንያቱም ቃሉን ፈርቶ ነበ ርና፤ የእግዚአብሔር ፍርድ በእርሱ ላይ ይመጣል ብሎ ፈርቶ ነበርና።

፲፪ ነገር ግን ካህናቱ በእርሱ ላይ ድምፃቸ ውን ከፍ በማድረግ ንጉሱን አዋርዷል በማ ለት ከሰሱት፣ ስለዚህ ንጉሱ በቁጣ በእርሱ ታወከ፣ እናም እርሱ ይገደል ዘንድ አሳ ልፎ ሰጠው።

፲፫ እናም እንዲህ ሆነ ወሰዱትና አሰሩት፣ እስኪሞት ድረስ በእስር ጭሮር አሰቃዩ ትም።

፲፬ እናም አሁን ነበልባሉ መለብለብ ሲጀ ምረው፣ እንዲህ በማለት ጮኸባቸው፥

፲፭ እነሆ፣ ለእኔ እንዳደረጋችሁት ሁሉ እንዲህ ይሆናል፣ ዘሮቻችሁ እኔ የተሰቃ የሁትን ሥቃይ፣ እንዲሁም [ሀ]በእሳት የመ ሞት ስቃይን፣ ብዙዎች እንዲሰቃዩ ያደር ጋሉ፤ እናም ይህ የሚሆነው በጌታ በአምላ ካቸው ደህንነት በማመናቸው ነው።

፲፮ እናም እንዲህ ይሆናል በክፋታችሁ የተነሳ በሁሉም አይነት በሽታ ትሰቃያላ ችሁ።

፲፯ አዎን፣ እናም በሁሉም ክንድ [ሀ]ትመ ታላችሁ፣ እናም የዱር መንጋ በዱርና ኃይለኛ አውሬዎች እንደሚነዱ፣ ወዲህና ወዲያ ትነዳላችሁም ትበተናላችሁም።

፲፰ እናም በዚያ ቀን ትታደናላችሁ፣ በጠ ላቶቻችሁ ክንድም ትወሰዳላችሁ፤ እናም ከዚያ በኋላ የሞትን ስቃይ [ሀ]በእሳት እኔ እን ደተሰቃየሁ ትሰቃያላችሁ።

፲፱ እንደዚህም እግዚአብሔር ህዝቡን በሚያጠፉት ላይ [ሀ]በቀልን ያደርጋል። አቤቱ አምላኬ ነፍሴን ተቀበል።

፳ እናም አሁን፣ አቢናዲ እነኚህን ቃላት በተናገረ ጊዜ፣ በእሳት ሞቶ ወደቀ፤ አዎን፣ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ባለመካዱ እን ዲሞት በመደረጉ፣ የቃሉን እውነታ በሞቱ አተመው።

ምዕራፍ ፲፰

አልማ በድብቅ ሰበከ—የጥምቀትን ቃል ኪዳን ገለፀ እናም በሞርሞን ውሃ አጠ መቀ—የክርስቶስን ቤተክርስቲያን አዋቀረ

፬ ሀ ቅ.መ.መ. ቅዱሳት መጻህፍት።
፰ ሀ ሞዛያ ፲፫፥፳፭፤ ፴፫–፴፬።
፲ ሀ አልማ ፷፥፲፫።
፲፭ ሀ ሞዛያ ፲፫፥፱–፲፤ አልማ ፳፭፥፬–፲፪።
፲፯ ሀ ሞዛያ ፳፩፥፩–፭፤ ፲፫።
፲፰ ሀ ሞዛያ ፲፱፥፲፰–፳።
፲፱ ሀ ቅ.መ.መ. በቀል።

እናም ካህናትን ሾመ—እነርሱም ራሳቸ ውን ረዱ እናም ህዝቡን አስተማሩ—አል ማና ህዝቡ ከንጉስ ኖህ ወደ ምድረበዳው ሸሹ። ከ፲፯፻፲–፲፯፻፳ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም አሁን እንዲህ ሆነ ከንጉስ ኖህ አገልጋዮች የሸሸው አልማ፣ ለኃጢአቱና ለጥፋቱ [a]ንስሃ ገባ፣ እናም በድብቅ ከህዝቡ መካከል ሄደና፣ የአቢናዲን ቃላት ማስተ ማር ጀመረ—

፪ አዎን፣ ወደፊት የሚመጣውን በተመለ ከተ፣ ደግሞም የሙታን ትንሳኤን በተመለ ከተና፣ በክርስቶስ [b]ሃይል፣ ስቃይና፣ ሞት ስለሚመጣው የህዝቦች [c]ቤዛነት፣ እናም ትንሳኤውና ወደሰማይ ማረጉን ማስተማር ጀመረ።

፫ እናም ቃሉን ለሚሰሙት ሁሉ አስተ ማረ። ንጉሱ እንዳያውቅም በድብቅ አስተ ማራቸው። እናም ብዙዎች ቃሉን አመኑት።

፬ እናም እንዲህ ሆነ ብዙዎች ስላመኑት ስሙን ከንጉሱ በመቀበል ሞርሞን ወደሚ ባል፣ በምድሪቱ ዳርቻ በመሆን በጊዜው ወይም በወቅቱ በዱር አራዊቶች ተወርሮ ወደነበር [d]ስፍራ ሄዱ።

፭ አሁን፣ የንፁህ ውሃ ምንጭ በሞርሞን ነበር፣ እናም አልማ ወደ ቦታው ሄደ፤ በው ሃውም አጠገብ በቀን እራሱን ንጉሱ እንዳ ያገኘው የሚደብቅበት ጥቅጥቅ ያሉ አጫ ጭር ዛፎች ነበሩ።

፮ እናም እንዲህ ሆነ የሚያምኑት ሁሉ ቃሉን ለመስማት ወደ እርሱ ሄዱ።

፯ እናም እንዲህ ሆነ ከብዙ ቀናት በኋላ የአልማን ቃል ለመስማት ሞርሞን በተባለ ስፍራ የተሰባሰቡ ብዙ ቁጥር ያላቸው ሰዎች ነበሩ። አዎን፣ በቃሉ ያመኑት ሁሉ ሊሰ ሙት ተሰበሰቡ። እናም [e]አስተማራቸው፣ ንስሃና፣ ቤዛነትን፣ እንዲሁም በጌታ ማመ ንንም ሰበከላቸው።

፰ እናም እንዲህ ሆነ እንዲህም አላቸው፥ እነሆ፣ የሞርሞን ውሃ ይህ ነው፣ (እንደዚ ህም ነበር የተጠሩት) እናም አሁን፣ እና ንተ ወደ እግዚአብሔር [f]በረት ለመምጣ ትና፣ ህዝቡ ትባሉ ዘንድ፣ እንዲሁም አን ዳችሁ የአንዳችሁን ሸክም ቀላል እንዲሆኑ ዘንድ ለመሸከም [g]ፈቃደኞች በመሆን [h]እን ደፈለጋችሁ፤

፱ አዎን፣ እናም ከሚያዝኑት ጋር ለማ ዘን፤ መፅናናትን ለሚፈልጉም ካፅናናች ኋቸው፤ እናም በሁሉም ጊዜ በሁሉም ነገ ርና፣ በምትኖሩበት ቦታዎች ሁሉ፣ እስከ ሞት ድረስ፣ [i]የእግዚአብሔር ምስክር በመ ሆን ትቆሙ ዘንድና፣ በጌታ ትድኑ ዘንድ፣ እናም [j]ዘለዓለማዊ ህይወትም ይኖራችሁ ዘንድና [k]የመጀመሪያውን ትንሳኤ ከሚያ ገኙት ጋርም ለመቆጠር ፈቃደኞች ከሆ ናችሁ—

፲ አሁን እላችኋለሁ፣ ይህ የልባችሁ ፍላ ጎት ከሆነ፣ እርሱን እንደምታገለግሉ እናም ትዕዛዛቱን እንደምትጠብቁ፣ እርሱም በእ ናንተ ላይ መንፈሱን በብዛት ያፈስባችሁ ዘንድ በፊቱ እንደምስክርነት ከእርሱ ጋር [l]ቃል ኪዳን በመግባት በጌታ ስም [m]ለመ ጠመቅ የሚያስቸግራችሁ ምንድን ነው?

፲፩ እናም አሁን ህዝቡ ይህንን አባባሉን በሰሙ ጊዜ፣ በደስታ አጨበጨቡ፣ እናም በደስታ ይህ የልባችን ፍላጎት ነው ብለው ጮኹ።

፲፪ እናም አሁን እንዲህ ሆነ አልማ ሔላ ምን ወሰደ፤ የመጀመሪያውም ሆኖና፣ ሄዶ በውሃው ውስጥ ቆመና እንዲህ ሲል ጮኸ፥ ጌታ ሆይ፣ በተቀደሰ ልብ ይህን ስራ ይሰራ ዘንድ፣ መንፈስህን በአገልጋይህ ላይ አፍስ።

፲፯ ፩ *a* ሞዛያ ፳፫፡፲–፳፡፲።
፪ *b* ቅ.መ.መ. የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ።
c ቅ.መ.መ. ቤዛ፣ ማዳን፣ ቤዛነት።
፬ *d* አልማ ፭፡፣ ፲፩–፲፫።
፭ *e* ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን።
f ቅ.መ.መ. ርህራሄ።
g ት.እና ቃ. ፭፡ ፴፯።
፱ *h* ቅ.መ.መ. መመስከር፣ ምስክር፣ የሚስዮን ስራ።
i ቅ.መ.መ. የዘለዓለም ህይወት።
j ሞዛያ ፲፭፡ ፳፭–፳፯።
k ቅ.መ.መ. ቃል ኪዳን።
l ፪ ኔፊ ፴፩፡ ፲፯።
ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣ መጥመቅ።

፲፫ እናም እነዚህን ቃላት ሲናገር፣ ᵐየጌታ መንፈስ በእርሱ ላይ ነበር፣ እናም እንዲህ አለ፡ ሄላም፣ ሁሉን ከሚገዛ አምላክ ᵃበተ ሰጠኝ ስልጣን፣ እስከሞት ድረስ እርሱን ለማገልገል ቃል ኪዳን እንደገባህ ምስክር ነት ᵇአጠምቅሀለሁ፤ እናም የጌታ መንፈስ በአንተ ላይ ይፍሰስ፤ እርሱንም ᶜከዓለም መፈጠር ጀምሮ ባዘጋጀው በክርስቶስ ᶜቤዛ ነት ዘለዓለማዊ ህይወት ይስጥህ።

፲፬ እናም አልማ ይህንን ቃል ከተናገረ በኋላ፣ አልማና ሄላም ሁለቱም በውሃው ውስጥ ᵐጠለቁ፤ እናም ተነሱና በመንፈስ ተሞልተው እየተደሰቱ ከውሃው ውስጥ ወጡ።

፲፭ እናም እንደገና፣ አልማ ሌላውን ወስዶ፣ ለሁለተኛ ጊዜም ወደ ውሃው ገባ፣ እናም ይኼኛውንም እንደመጀመሪያው አጠመቀው፤ ነገር ግን ራሱ በድጋሚ ውኃ ውስጥ አልጠለቀም ነበር።

፲፮ እናም ወደ ሞርሞን ስፍራ የሄዱትን ማናቸውንም በዚህ ሁኔታ ያጠምቅ ነበር፣ በቁጥርም ወደ ሁለት መቶ አራት ነፍስ ገደማ ነበሩ፤ አዎን፣ እናም በሞርሞን ውሃ ᵐተጠምቀው ᵃበእግዚአብሔርም ፀጋ ተሞ ልተው ነበር።

፲፯ እናም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የእግዚአ ብሔር ቤተክርስቲያን፣ ወይንም ᵐየክርስ ቶስ ቤተክርስቲያን ተብለው ተጠሩ። እናም እንዲህ ሆነ በእግዚአብሔር ኃይልና ስልጣን የተጠመቀ ማንኛውም ወደ እርሱ ቤተክር ስቲያን ይጨመራል።

፲፰ እናም እንዲህ ሆነ አልማ፣ ᵐከእግዚ አብሔር ስልጣንን ኖሮት ካህናትን ᶜሾመ፤ እንዲያውም አንድ ካህንም ቢሆን ሀምሳዎ ችን እንዲያስተምሩና፣ ስለእግዚአብሔር መንግስት ተገቢ የሆኑትን ነገሮች ᵃእንዲ ያስተምሩ ᶜሾማቸው።

፲፱ እናም እርሱ ካስተማራቸውና በቅዱ ሳን ነቢያቱ አፍ ከተናገራቸው ነገሮች በቀር ምንም እንዳያስተምሩ አዘዛቸው።

፳ አዎን፣ ህዝቡን ስላዳነው ጌታ ንስሃንና እምነትን ካልሆነ በቀር ምንም ᵐእንዳይሰ ብኩ አዘዛቸው።

፳፩ እናም አንዱ ከሌላኛው ᵐእንዳይጣላ፣ ነገር ግን አንድ እምነትና፣ አንድ ጥምቀት ይዘው፣ ᵃበአንድ ዓይን እንዲተያዩ፣ ልባ ቸው በአንድ ላይ ᵃበአንድነትና፣ አንዱ ሌላኛውን ባለው ፍቅር እንዲጣበቁ አዘ ዛቸው።

፳፪ እና እንደዚህም እንዲሰብኩ አዘዛ ቸው። እንደዚህም ᵐየእግዚአብሔር ልጆች ሆኑ።

፳፫ እናም ᵐየሰንበትን ቀን እንዲያከብ ሩና፣ እንዲቀድሱት፣ ደግሞም ለጌታ ለአ ምላካቸው በየቀኑ ምስጋናን እንዲያቀርቡ አዘዛቸው።

፳፬ እናም ደግሞ እርሱ የሾማቸው ካህናት እራሳቸውን ለመርዳት በእጃቸው ᵐእንዲ ሰሩ አዘዛቸው።

፳፭ እናም ህዝቡን በአንድ ላይ በመሰ ብሰብ ለማስተማርና፣ ጌታ ᵐአምላካቸ ውን ለማምለክ ከሳምንቱ አንዱ ቀን መር ጠዋል፣ ደግሞም እንደቻሉ፣ ሁልጊዜም እራሳቸውን ይሰበስባሉ።

፳፮ እናም ካህናቱ ለኑሮአቸው ድጋፍን ለማግኘት በህዝቡ ላይ ጥገኛ አልነበሩም፣

፲፫ ᵐ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
ᵃ እ.አ. ፩፡፲።
ቅ.መ.መ. ክህነት።
ᵇ ᶜ ኔፊ ፲፩፡፳፫–፳፮፣ ት. እና ቃ. ፳፡ ፳፪–፳፬።
ᶜ ሙሴ ፬፡ ፪፣ ፲፡ ፱።
ᵐ ቅ.መ.መ. ቤዛ፣ ማዳን፣ ቤዛነት።

፲፬ ᵐ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣ መጥመቅ—በማጥለቅ መጥመቅ።

፲፯ ᵐ ሞዛያ ፳፭፡፲፰።
ᵃ ቅ.መ.መ. ጸጋ።

፲፰ ᵐ ᶜ ኔፊ ፳፩፡ ፳፪፣ ፳፯፡ ፫–፰።
ᵃ ᶜ ኔፊ ፲፩፡ ፳፫–፳፡ ᶜ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን።

፲፱ ᵐ ᶜ ቅ.መ.መ. ክህነት።
ᵃ ᶜ ቅ.መ.መ. ማስተማር፣ አስተማሪ።

፳ ᵐ ት. እና ቃ. ፲፭፡ ፮፣ ፲፡ ፲፬፡ ፲፭–፲፯።

፳፩ ᵐ ᶜ ኔፊ ፲፩፡ ፳፰–፳፡ ᶜ ቅ.መ.መ. ጸብ።
ᵃ ማቴ. ፮፡ ፳፪፣ ት. እና ቃ. ፹፰፡ ፳፯–፳፰።
ᵃ ᶜ ቅ.መ.መ. አንድነት።

፳፪ ᵐ ሞዛያ ፭፡ ፭–፯፣ ሙሴ ፮፡ ፳፡ ፳–፳፫።

፳፫ ᵐ ሞዛያ ፲፫፡ ፲፮–፲፱፣ ት. እና ቃ. ፶፱፡ ፱–፲፪።

፳፬ ᵐ የሐዋ. ፳፡ ፴፫–፴፭፣ ሞዛያ ፳፯፡ ፫–፭፣ አልማ ፩፡ ፳፯።

፳፭ ᵐ ቅ.መ.መ. ማምለክ።

ነገር ግን [ሀ]የእግዚአብሔርን ዕውቀት በማ
ግኘት በመንፈስ ጠንክረው ያድጉ ዘንድ፣
በእግዚአብሔር ኃይልና ሥልጣን ለማስተ
ማር [ለ]የእግዚአብሔርን ፀጋ ይቀበሉ ነበር።
፳፯ እናም በድጋሚ አልማ የቤተክርስቲ
ያኑ አባላት [ሀ]እያንዳንዳቸው ባላቸው መጠን
እንዲያካፍሉ አዘዘ፤ በብዛት ካለው በብዛት
ያካፍል፤ ትንሽ ያለውም ግን ትንሽ ይፈለ
ግበታል፣ የሌለውም ይሰጠዋል።
፳፰ እናም ወደ እግዚአብሔርና፣ ድጋፍ
ለሚያስፈልጋቸው ካህናት፣ አዎን፣ እናም
ለማንኛውም ችግረኛ ለሆነ፣ ለተራቆተ
ነፍስ ባላቸው መልካም ፍላጎት ሀብታቸ
ውን በነፃ ፈቃዳቸው እንደዚህም ማካፈል
ይገባቸዋል።
፳፱ እናም በእግዚአብሔር በመታዘዝ እን
ዲህ አላቸው፥ እናም እንደፍላጎታቸውና
ፈቃዳቸው አንዱ ለሌላው በአለማዊና መን
ፈሳዊ አመለካከት ያላቸውን [ሀ]በመካፈል
በእግዚአብሔር ፊት [ለ]በቅንነት ተራመዱ።
፴ እናም አሁን እንዲህ ሆነ ይህ ሁሉ የሆ
ነው በሞርሞን ነው፣ አዎን፣ [ሀ]በሞርሞን
ውኃ አጠገብ ባለው ጫካ በሞርሞን ውኃ
አጠገብ ነበር፤ አዎን፣ የሞርሞን ስፍራ፣
የሞርሞን ውኃ፣ የሞርሞን ጫካ፣ ቤዛቸ
ውን ለማወቅ በመጡበት ዐይን እንዴት
ውብ ናቸው፤ አዎን፣ እናም እንዴት የተ
ባረኩ ናቸው፣ ለዘለዓለም እርሱን ለማመ
ስገን ይዘምራሉና።
፴፩ እናም እነዚህ ሁሉ የተደረጉት ንጉሱ
እንዳያውቃቸው በምድሪቱ [ሀ]ዳርቻ ነው።
፴፪ ነገር ግን እነሆ፣ እንዲህ ሆነ ንጉሱ፣
በህዝቡ መካከል እንቅስቃሴ በመመልከት፣
አገልጋዮቹን እንዲመለከቷቸው ላከ። ስለ
ዚህ የጌታን ቃል ለመስማት አብረው በተ
ሰበሰቡበት ቀን በንጉሱ ተገኙ።
፴፫ እናም አሁን ንጉሱ አልማ ህዝቡ በእ
ርሱ ላይ እንዲያምፅ ያውካል አለ፤ ስለ
ዚህ እነርሱን እንዲያጠፉአቸው ወታደሮ
ቹን ላከ።
፴፬ እናም እንዲህ ሆነ አልማና የጌታ
ህዝብ የንጉሱን ወታደሮች መምጣት
[ሀ]አወቁ፤ ስለዚህ ድንኳናቸውንና ቤተሰቦ
ቻቸውን ወሰዱና፣ ወደ ምድረበዳው ሸሹ።
፴፭ እናም በቁጥር አራት መቶ ሀምሳ ነፍስ
ገደማ ነበሩ።

ምዕራፍ ፲፱

ጌዴዎን ንጉስ ኖህን ለመግደል ፈለገ—ላማናውያን ምድሪቱን ወረሩ—ንጉስ ኖህ በእሳት ሞተ—ሊምሂ እንደ ግብር ከፋይ ንጉስ ገዛ። ከ፻፵፭–፻፳፩ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ የጌታን ህዝብ በከንቱ
ከፈለጉ በኋላ የንጉሱ ወታደሮች ተመለሱ።
፪ እናም አሁን እነሆ፣ የንጉሱ ኃይል በመ
ቀነሳቸው፣ ትንሽ ነበሩ፤ በቀሪው ህዝብ
መካከል መከፋፈል ተጀመረ።
፫ እናም ትንሹ ክፍል ንጉሱን ማስፈራ
ራት ጀመረ፤ እናም በመካከላቸው ታላቅ
ፀብ ተጀመረ።
፬ እናም አሁን በመካከላቸው ጌዴዎን
የሚባል ሰው ነበር፣ እርሱም ጠንካራ ሰውና
ለንጉሱ ጠላት በመሆኑ፣ ስለዚህ ጎራዴውን
መዘዘና ንጉሱን እንደሚገድለው በቁጣው
ማለ።
፭ እናም እንዲህ ሆነ ከንጉሱ ጋር ተዋጋ፤
ንጉሱም እንደሚያሸንፈው በተመለከተ
ጊዜ፣ ሸሸና፣ ሮጠ፣ እና በቤተ መቅደሱ
አጠገብ በሚገኘው [ሀ]ግንብ ላይ ወጣ።
፮ እናም ጌዴዎን ተከተለውና ንጉ
ሱን ለመግደል ወደ ግንቡ ተጠጋ፣ እናም
ንጉሱ አይኑን በዚህና በዚያ ተመለከተና
በሸምሎን ምድር ላይ አይኑን ጣለ፣ እናም
እነሆ፣ የላማናውያን ወታደሮች በምድሪቱ
ዳርቻ እንደ ነበሩ ተመለከተ።

፳፯ ሀ ቅ.መ.መ. እውቀት።
ለ ቅ.መ.መ. ጸጋ።
፳፯ ሀ የሐዋ. ፪፥ ፵፬–፵፭፤
፬ ኔፊ ፩፥ ፫።
፳፱ ሀ ቅ.መ.መ. በጎ ድርገት።
ለ ቅ.መ.መ. መራመድ፣
ከእግዚአብሔር ጋር
መራመድ (መሄድ)።
፴ ሀ ሞዛያ ፳፮፥ ፲፭።
፴፩ ሀ ሞዛያ ፲፰፥ ፬።
፴፬ ሀ ሞዛያ ፳፫፥ ፩።
፲፱ ፭ ሀ ሞዛያ ፲፩፥ ፲፪።

፯ እናም አሁን ንጉሱ በጭንቀት እንዲህ በማለት ጮኸ፡ ጌዴዎን፣ ህይወቴን አት ርፈው፣ ላማናውያን በእኛ ላይ መጥተዋ ልና፣ እናም ያጠፉናል፤ አዎን፣ ህዝቤንም ያጠፉታል።

፰ እናም አሁን ንጉሱ ለህይወቱ እንዳሰ በው ያህል ለህዝቡ አላሰበም ነበር፤ ይሁን እንጂ፣ ጌዴዎን ህይወቱን አተረፈለት።

፱ እናም ንጉሱ ህዝቡ ከላማናውያን እንዲ ሸሽ አዘዘ፤ እርሱም ራሱ ከፊታቸው ሄደ፣ እናም እነርሱ ከሴቶቻቸውና ከልጆቻቸው ጋር ወደ ምድረበዳ ሸሹ።

፲ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን ተከተ ሉአቸውና፣ ደረሱባቸው፣ ይገድሉአቸ ውም ጀመሩ።

፲፩ አሁን እንዲህ ሆነ ንጉሱ ሁሉም ወን ዶች ሚስቶቻቸውንና ልጆቻቸውን እን ዲተው እናም ከላማናውያን ፊት እንዲ ሸሹ አዘዘ።

፲፪ አሁን ትተዋቸው ያልሄዱ ብዙዎች ነበሩ፣ ነገር ግን ከእነርሱ ጋር መቆየትና መጥፋት ፈለጉ። እናም የተቀሩት ሚስቶ ቻቸውንና ልጆቻቸውን ትተው ሸሹ።

፲፫ እናም እንዲህ ሆነ ከሚስቶቻቸውና ከልጆቻቸው ጋር የቀሩት፣ ቆንጆዎቹ ሴቶች ልጆቻቸው ላማናውያን እንዳይገ ድሉአቸው እንዲለምኑ ወደፊት እንዲቆሙ አስደረጉ።

፲፬ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን በሴቶ ቻቸው ውበት በመማረካቸው አዘኑላቸው።

፲፭ ስለዚህ ላማናውያን ህይወታቸውን አተረፉላቸውና፣ ማረኩአቸው፣ እንዲ ሁም ወደኔፊ ምድር መለሱአቸው፣ እናም ንጉስ ኖህን ለላማናውያን ካቀረቡ፤ ንብ ረቶቻቸውን፣ እንዲሁም ካሉአቸው ሁሉ ግማሹን፣ ከወርቃቸው ግማሹንና፣ ከብራ ቸው፣ እናም ከሁሉም ከከበሩ ነገሮቻቸው አሳልፈው ከሰጡ ምድሪቱን እንደሚይዙ ተስማምተው ሰጡአቸው፣ በዚህም በየዓ መቱ ለላማናውያን ንጉስ ግብርን እንዲከ ፍሉ አደረጉአቸው።

፲፮ እናም አሁን በምርኮ ከተወሰዱት መካከል ስሙ ᐸሊምሂ የተባለ የንጉሱ ልጆች የሆነ አንድ ልጅ ነበር።

፲፯ እናም አሁን ሊምሂ አባቱ እንዳይጠፉ ፈልጎ ነበር፤ ይሁን እንጂ፣ ሊምሂ የአባቱን ክፋት የማያውቅ አልነበረም፣ እርሱ ራሱ ፃድቅ ሰው ነበርና።

፲፰ እናም እንዲህ ሆነ ጌዴዎን ንጉሱንና ከእርሱ ጋር ያሉትን ለማግኘት በሚስጥር ወደ ምድረበዳው ሰዎችን ላከ። እናም እን ዲህ ሆነ ከንጉሱና ከካህናቱ በስተቀር በም ድረበዳ ውስጥ ከሰዎች ጋር ተገናኙ።

፲፱ አሁን ሚስቶቻቸውና ልጆቻቸው፣ እናም ደግሞ ከእነርሱ ጋር የተቀሩት ቢገ ደሉ በቀልንና ደግሞ ከእነርሱ ጋር መጥፋ ትን በመፈለግ ወደ ኔፊ ምድር እንደሚመ ለሱ በልባቸው ምለው ነበር።

፳ እናም ንጉሱ መመለስ እንደሌለባቸው አዘዛቸውና፣ በንጉሱ ተቆጡ፣ ᐸበእሳትም እስኪሞት እንኳን እንዲሰቃይ አደረጉ።

፳፩ እናም ካህናቱን ደግሞ ለመውሰ ድና፣ ለመግደል ፈለጉ፣ እነርሱም ሸሽ ተው አመለጡአቸው።

፳፪ እናም እንዲህ ሆነ ወደ ኔፊ ምድር እየተመለሱ እያሉ፣ እናም የጌዴዎንን ሰዎች አገኙ። የጌዴዎን ሰዎችም በል ጆቻቸውና በሚስቶቻቸው ላይ ስለተ ፈፀመው ነገር ሁሉ ነገሯቸው፤ እንዲ ሁም ለላማናውያን ካላቸው ሁሉ አንድ ሁለተኛውን ግብር ከከፈሉ ላማናውያን ምድሩን እንዲይዙ እንደፈቀዱላቸው ነገሯቸው።

፳፫ እናም ህዝቡ ለጌዴዎን ህዝብ ንጉሱን እንደገደሉትና፣ ካህናቱ ወደ ጥልቅ ምድ ረበዳው እንደሸሹ ነገሩአቸው።

፳፬ እናም እንዲህ ሆነ ስነስርዓቱ ካለቀ በኋላ፣ ወደኔፊ ምድር በደስታ ተመለሱ፣ ምክንያቱም ሚስቶቻቸውና ልጆቻቸው አልተገደሉም ነበርና፤ እናም ለጌዴዎን በንጉሱ ላይ ያደረጉትን ነገሩት።

፳፭ እናም እንዲህ ሆነ የላማናውያን

ንጉስ ህዝቡ እንደማይገድሉአቸው ″መሀላ ፈፀመ።

፳፤ እናም ደግሞ ሊምሂ የንጉስ ልጅ በመሆኑ፣ ″በህዝቡም በገዥነት በመሾሙ፣ ህዝቡ ካለው ግማሹን ያህል ግብር እንደሚ ከፍሉ ለላማናውያን ንጉስ መሃላ አደረገ።

፳፤ እናም እንዲህ ሆነ ሊምሂ መንግስት መመስረት እናም በህዝቡ መካከል ሰላምን መመስረት ጀመረ።

፳፤ እናም የሊምሂ ህዝብ በምድር ውስጥ እንዲጠብቁ፣ ወደ ምድረበዳው እንዳይ ሸሹ፣ የላማናውያን ንጉስ በሀገሪቱ ዙሪያ ጠባቂዎችን አስቀመጠ፤ እናም ከኔፋውያን በሚቀበለው ግብርም ጠባቂዎቹን ደገፈ።

፳፤ እናም አሁን ንጉስ ሊምሂ ያለማቋረጥ ለሁለት ዓመታት በመንግስቱ ላይ ሰላም ነበረው፣ ላማናውያንም አላበሳጨአቸውም እንዲሁም ሊያጠፉአቸው አልፈለጉም።

ምዕራፍ ፳

አንዳንድ የላማናውያን ሴት ልጆች በኖህ ካህናት ተጠልፈው ነበር—ላማናውያን በሊምሂና በህዝቡ ላይ ጦርነት አደረጉ—የላማናውያን ሠራዊቶች አሸነፉቸውና አረጋጓቸው። ከ፲፯–፲፳፫ ም.ዓ. ገደማ።

፩ አሁን በሻምሎን የላማናውያን ሴት ልጆች ለመዝፈንና ለመደነስ እናም እራ ሳቸውን ለማስደሰት በአንድነት የሚሰበስ ቡበት ስፍራ ነበር።

፪ እናም እንዲህ ሆነ በጥቂት የሚቆጠሩ እራሳቸውን በአንድነት ለመዝፈንና ለመ ደነስ አንድ ቀን አሰባስበው ነበር።

፫ እናም አሁን የንጉስ ኖህ ካህናት ወደ ኔፊ ከተማ ለመመለስ በማፈር፣ አዎን፣ እናም ደግሞ ህዝቡ ይገድለናል ብለው ስለፈሩ፣ ስለዚህ ወደ ሚስቶቻቸውና ልጆቻቸው ለመመለስ አልደፈሩም።

፬ እናም በምድረበዳ ውስጥ በመቅረታቸ ውና፣ የላማናውያን ሴት ልጆችን በማግኘ ታቸው ተኝተው ጠበቁአቸው፣

፭ እናም ጥቂቶች ለመደነስ በአንድ ላይ በተሰበሰቡ ጊዜ፣ ከተደበቁበት ስፍራ ወጡና ጠለፉአቸው እናም ወደ ምድ ረበዳው ወሰዱአቸው፤ አዎን፣ የላማና ውያን ሀያ አራት ሴት ልጆችን ወደ ምድ ረበዳው ወሰዱአቸው።

፮ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን የሴት ልጆቻቸውን መጥፋት ሲያውቁ፣ ይህን ያደረጉት የሊምሂ ህዝብ ናቸው ብለው በማሰብ በሊምሂ ህዝብ ተቆጡ።

፯ ስለዚህ ወታደሮቻቸውን ላኩባቸው፣ አዎን፣ ንጉሱም ራሱ እንኳን ቢሆን ከህ ዝቡ ፊት ሄደ፤ እናም የሊምሂን ህዝብ ለማ ጥፋት ወደ ኔፊ ምድር ሄዱ።

፰ እናም አሁን ሊምሂ ከግንቡ ላይ ተመ ለከታቸውና፣ ለጦርነት ሁሉንም ዝግጅ ታቸውን ተመለከተ፤ ስለዚህ ህዝቡን በአ ንድ ላይ ሰበሰበና፣ እናም በመስኩ ላይና በጫካው መሸገው ጠበቁ።

፱ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን በመጡ ጊዜ፣ የሊምሂ ህዝቦች ይጠብቁበት ከነበ ረበት ስፍራ ያጠቁአቸውና፣ ይገድሉአ ቸው ጀመር።

፲ እናም እንዲህ ሆነ ጦርነቱ እጅግ አሰቃቂ ሆነ፤ ልክ አንበሳዎች ለአደኖቻቸው እንደ ሚጣሉም አይነት ነበርና።

፲፩ እናም እንዲህ ሆነ የሊምሂ ህዝብ ላማናውያንን ከፊታቸው ማባረር ጀመሩ፤ ይሁን እንጂ እንደ ላማናውያን ግማሹን እን ኳን ያህል አይበዙም ነበር። ነገር ግን ለህይ ወታቸው፣ እናም ለሚስቶቻቸውና፣ ለል ጆቻቸው ″ታገሉ፤ ስለዚህ ለራሳቸው እን ደዘንዶው ለመዋጋት ጥረት አድርገዋል።

፲፪ እናም እንዲህ ሆነ ከሙታን መካከል የላማናውያንን ንጉስ አገኙ፤ ሆኖም እርሱ ገና አልሞተም ነበር፣ ቆስሎ ነበር፣ እናም የህዝቡም ሽሽት ፈጣን ስለነበር በመሬቱም ላይ ወድቆ ነበር።

፲፫ እናም ወሰዱትና ቁስሉን አሰሩለት፣ እንዲሁም ከሊምሂ ፊት አመጡት፣ እናም እንዲህ አሉ፤ እነሆ፣ የላማናውያን ንጉስ

ይኸውና፣ በመቁሰሉም ከሙታኖቻቸው መካከል ወደቀና፣ ጥለውት ሄዱ፤ እናም እነሆ፣ በፊትህ አመጣነው፤ እናም አሁን እንግደለው።

፲፡ ነገር ግን ሊምሂ እንዲህ አላቸው፡ አትግደሉት፣ ነገር ግን እኔ እንዳየው ወደ ዚህ ስፍራ አምጡት። እነርሱም አመጡት። እናም ሊምሂ እንዲህ አለው፡ አንተን ከህ ዝቤ ጋር በጦርነት ለመምጣት ያነሳሳህ ምን ድን ነው? እነሆ፣ ህዝቤ ለአንተ ያደረግሁ ትን መሃላ አላፈረሱም፤ ስለዚህ፣ ለምን አንተ ለህዝቤ ያደረግኸውን ᐧመሃላ ታፈ ርሳለህ?

፲፡፩ እናም አሁን ንጉሱ እንዲህ አለ፡ ህዝብህ የህዝቤን ሴቶች ልጆችን ስለወሰዱ መሃላዬን አፈረስሁ፤ ስለዚህ፣ በቁጣዬ ህዝቤ ከህዝብህ ላይ በጦርነት እንዲመጡ አድርጌአለሁ።

፲፡፲፪ እናም አሁን ሊምሂ ይህንን በተመለ ከተ ምንም አልሰማም ነበር፤ ስለዚህ እን ዲህ አለ፡ ከህዝቤ መካከል እፈልጋለሁ እናም ይህንን ያደረገ ይጠፉል። ስለዚህ በህዝቡ መካከል እንዲፈልጉ አደረገ።

፲፡፲፫ አሁን ᐧጌዴዎን እነዚህን ነገሮች በሰማ ጊዜ፣ እርሱ የንጉሱ ካፒቴን በመ ሆኑ፤ ሄዶም ለንጉሱ እንዲህ አለው፡ እባክ ህን እማፀንሃለሁ፣ እናም ይህን ህዝብ አት ፈትሽ፣ ህዝቡንም በዚህ ሀላፊ አታድርጋ ቸው።

፲፡፲፡ ይህ ህዝብ ሊያጠፏቸው የፈለጓቸውን የአባትህን ካህናት አታስታውስምን? እናም በምድረበዳስ አይደሉምን? እናስ የላማና ውያንን ሴት ልጆች የሰረቁት እነርሱ አይ ደሉምን?

፲፡፲፱ እናም አሁን፣ እነሆ እናም ለህ ዝቡ እንዲነግራቸውና ወደ እኛ እንዲረ ጋጉ እነዚህን ነገሮች ለንጉሱ ንገር፤ እነ ሆም በእኛ ላይ ለመምጣት ዝግጅታቸውን አጠናቀዋል፤ እነሆም፣ ደግሞ ከእኛ ጥቂ ቶቹ ነንና።

፲፡ እናም እነሆ፣ ከብዙ ሰራዊቶቻቸው ጋር መጡ፣ እናም ንጉሱ ካላረጋጋቸው በስተ ቀር እኛ እንጠፋለን።

፲፡፳ አቢናዲ በእኛ ላይ የተነበያቸው ቃላት ᐧአልተፈፀሙምን—እናም ይህ ሁሉ የሆነ በት ምክንያት የጌታን ቃል ባለመስማታ ችን፣ እናም ከክፋታችንስ ባለመመለሳችን አይደለምን?

፲፡፳፪ እናም እንግዲህ ንጉሱን እናረጋጋው እናም የገባውን መሃላ እንፈፅም፤ ምክንያ ቱም ህይወታችንን ከምናጣ በባርነት ሥር ብንሆን ይሻለናል፤ ስለዚህ የብዙ ደም መፋሰሱን እናቁመው።

፲፡፳፫ እናም እንግዲህ ሊምሂ ስለአባቱና ወደ ምድረበዳው ስለሸሹት ᐧካህናት ለን ጉሱ ነገረው፣ እናም ሴቶች ልጆቻቸው የመውሰድ ጥፋተኛነትን በተመለከተ በእ ነርሱ ላይ ጣለው።

፲፡፳፬ እናም እንዲህ ሆነ ንጉሱ ወደ ህዝቡ ተረጋጋ፣ እንዲህም አላቸው፡ ከህዝቤ ጋር ለመገናኘት መሳሪያዎችን ሳንይዝ እንሂድ፤ እናም ህዝቤ ህዝባችሁን እንደማይገድልም መሃላ እምልላችኋለሁ።

፲፡፳፭ እናም እንዲህ ሆነ ንጉሱን ተከተ ሉትና፣ መሳሪያቸውን ሳይዙ ላማናው ያንን ለማግኘት ሄዱ። እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያንን አገኙአቸው፤ የላማናውያ ንም ንጉስ ከፊታቸው በመስገድ ስለሊምሂ ህዝብ ለመነ።

፲፡፲፮ እናም ላማናውያን የሊምሂን ህዝብ ያለ ጦር መሳሪያ መሆናቸውን በተመለ ከቱ ጊዜ፣ ᐧአዘኑላቸውና፣ ወደ እነርሱ ተረጋጉ፣ ከንጉሳቸውም ጋር በሰላም ወደ ራሳቸው ምድር ተመለሱ።

ምዕራፍ ፳፩

የሊምሂ ህዝብ በላማናውያን ተመቱ እናም ተሸነፉ—የሊምሂ ህዝብ አምንን አገኙ፣ እናም ተለወጡ—ለአምን ስለሃያ አራቱ

፲፡፩ ᐧ ሞዛያ ፲፱፡፳፫–፳፯። ፲፡፲፪ ᐧ ሞዛያ ፲፡፩–፰። ፲፡፲፭ ᐧ ሞዛያ ፲፡፲፡–፲፡
፲፡፲፱ ᐧ ሞዛያ ፲፡፩–፳። ፲፡፳ ᐧ ሞዛያ ፲፡፩–፰፡ ፳፡፲፡–፲፡ ᐧ ሞዛያ ፲፡፳፡ ፳፡፲፡ ᐧ ቅ.መ.መ. ርህራሄ።

የያሬዳውያን ሰሌዳዎች ነገሩት። ከ፲፳፳፪–፲፳፳፩ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ ሊምሂና ህዝቡ ወደ ኔፊ ከተማ ተመለሱና፣ በምድሪቱ ላይ እን ደገና በሰላም መኖር ጀመሩ።

፪ እናም እንዲህ ሆነ ከብዙ ቀናት በኋላ ላማናውያን በኔፋውያን ላይ በድጋሚ በቁጣ ተነሳሱና፣ በዙሪያው ወዳለው ምድር ድን በር መምጣት ጀመሩ።

፫ አሁን ንጉሱ ለሊምሂ በመማሉ ምክን ያት ሊገድሏቸው አልደፈሩም፤ ነገር ግን ᵐበጉንጮቻቸው ላይ መቱአቸው፣ እናም ስልጣናቸውን ተጠቀሙባቸው፤ እናም በትከሻቸው ከባድ ᵃሸክም አስቀመጡ ባቸውና እንደደንቆሮ አህያ ይነዱአቸው ጀመር—

፬ አዎን፣ ይህ ሁሉ የሆነው የጌታ ቃል ይፈፀም ዘንድ ነበር።

፭ እናም አሁን የኔፋውያን ስቃይ ታላቅ ነበር፣ እናም ላማናውያን በሁሉም አቅጣጫ ስለከበቡአቸው ከእጃቸው የሚያስለቅቁበት ምንም መንገድ አልነበረም።

፮ እናም እንዲህ ሆነ በስቃያቸው ምክን ያት ህዝቡ በንጉሱ ላይ አቤቱታ ማቅረብ ጀመሩ፤ ከእነርሱም ጋር እንደገናም ለመ ዋጋት ፈለጉ። እናም በአቤቱታቸው ንጉ ሱን በአስከፊ ሁኔታ አሰቃዩት፤ ስለዚህ እነ ርሱም እንደፍላጎታቸው እንዲያደርጉ ፈቀ ደላቸው።

፯ እናም በድጋሚ ተሰባሰቡና፣ መሳሪያ ዎቻቸውን ታጠቁ፣ እናም ላማናውያኖችን ከምድራቸው ለማባረር ወደ እነርሱ ሄዱ።

፰ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን መት ተው መለሱአቸውና፣ ብዙዎቻቸውን ገደ ሉአቸው።

፱ እናም አሁን በሊምሂ ህዝብ መካከል ታላቅ ᵐልቅሶና ዋይታ ነበር፤ ባሏ የሞተባት ለባሏ አለቀሰች፣ ሴትና ወንድ ልጆች ለአ ባታቸው አለቀሱ፣ እናም ወንድሞች ለወ ንድሞቹ አዘኑ።

፲ አሁን በምድሪቱ ብዙ ባልቴቶች ነበሩ፣ እናም ከቀን ወደ ቀንም በኃይል ያለቅሱ ነበር፣ ታላቅ የሆነ የላማናውያን ፍርሃት በእነርሱ ላይ መጥቶ ነበርና።

፲፩ እናም እንዲህ ሆነ የማያቋርጠው ጩኸታቸው ቀሪዎቹን የሊምሂን ህዝብ በላ ማናውያኖች ላይ እንዲቆጡ አወካቸው፣ እናም በድጋሚ ለውጊያ ሄዱ፣ ነገር ግን በድጋሚ ተከላክለው መለሱአቸው፣ ብዙ ህይወት ጠፋባቸው።

፲፪ አዎን፣ ለሶስተኛ ጊዜ በድጋሚ ሄዱ፣ እንደገናም እንደዚያው ሆነባቸው፤ እናም ያልተገደሉት በድጋሚ ወደ ኔፊ ከተማ ተመለሱ።

፲፫ እናም ትቢያ እስኪሆኑ ድረስ እራሳቸ ውን ዝቅ አደረጉ፣ እናም እንደጠላቶቻቸው ፍላጎት ወዲህና ወዲያ እንዲወስዱአቸውና እንዲያሸክሙአቸው እራሳቸውን ወደ ባር ነት ቀንበር በማስገደድ እንዲቀጡ እራሳቸ ውን አሳልፈው ሰጡ።

፲፬ እናም እስከ ጥልቅ ትህትና ድረስ ራሳ ቸውን ᵐትሁት አደረጉ፤ እናም ወደ እግዚ አብሔር በኃይል ጮሁ፤ አዎን፣ ከስቃያ ቸው ያስለቅቃቸው ዘንድ ቀኑን ሙሉ ወደ አምላካቸው ጮኸዋል።

፲፭ እናም አሁን በክፋታቸው የተነሳ ጌታ ጩኸታቸውን ለማዳመጥ ᵐዘግይቷል፤ ይሁን እንጂ፣ ጌታ ፀሎታቸውን ሰምቷል፣ ሸክማቸውንም ማቃለል እንዲጀምሩ የላ ማናውያንን ልብ ማራራት ጀመረ፤ ይሁን እንጂ ጌታ ከባርነት እነርሱን የማዳኑ አስፈ ላጊነት ውሳኔው ላይ አላደረሰም።

፲፮ እናም እንዲህ ሆነ በምድሪቱ ቀስ በቀስ መበልፀግ ጀመሩ፣ እናም በርሃብ እንዳይ ሰቃዩ እህልና መንጋዎችን እና ተክሎችን በብዛት ማምረት ጀመሩ።

፲፯ አሁንም ከወንዶቹ የሚበልጡ ብዙ

፳፩ ፲ ሀ ሞዛያ ፲፪፡ ፪።
ለ ሞዛያ ፲፪፡ ፭።
፱ ሀ ሞዛያ ፲፪፡ ፱።
ᵐ ልቅሶ ዋይታ ነበር፤ ባሏ የሞተባት ለባሏ አለቀሰች፣ ሴትና ወንድ ልጆች ለአ ባታቸው አለቀሱ፣ እናም ወንድሞች ለወ ንድሞቹ አዘኑ።

፲፩ ሀ ሞዛያ ፳፱፡ ፳።
ᵐ ዘግይቷል ትሁት፣ ትሕትና።
ᵐ ትሁት ትሕትና።
፲፭ ሀ ምሳ. ፲፭፡ ፳፱፤
ᵐ ዘግይቷል ትሁት፣ ትሕትና።
ᵐ ትሁት ትሕትና።
ሞዛያ ፲፭፡ ፳፫–፳፭፣
ት. እና ቃ. ፲፭፡ ፯–፱።

ቁጥር ያላቸው ሴቶች ነበሩ፣ ስለዚህ ንጉስ ሊምሂ ᵐባሎቻቸው ለሞቱባቸውና ለልጆ ቻቸው በረሃብ እንዳይጠፉ ማንኛውም ሰው እነርሱን ለመደገፍ ያለውን ᵃእንዲያካፍል አዘዘ፤ እናም ይህን ያደረገው የተገደሉት ቁጥራቸው ብዙ በመሆኑ ነበር።

፲፰ አሁን የሊምሂ ህዝቦች እስከሚቻላ ቸው ድረስ በአንድነት በቡድን ተጠጋግ ተው፣ እናም እህሎቻቸውና መንጋዎቻ ቸውን ይጠብቃሉ፤

፲፱ እናም ንጉሱ ራሱ፤ በዘዴ በላማናው ያን እጅ እወድቃለሁ በማለት ይፈራ ስለ ነበር፣ ጠባቂዎቹን ካልወሰደ በቀር ከከተ ማው ግንብ ውጪ የራሱን ደህንነት አያ ምንም።

፳ እናም የላማናውያን ᵐሴት ልጆችን የሰ ረቁትንና ታላቅ ጥፋት በእነርሱ ላይ እንዲ መጣ ያደረጉትን፣ ወደ ምድረበዳው የሸሹ ትን ካህናት በዘዴም ይወስዷቸው ዘንድ ህዝቡ በዙሪያው ያለውን ምድር እንዲጠ ብቅ አደረገ።

፳፩ ይቀጡአቸው ዘንድ ፍላጎት ነበራቸ ውና፤ በምሽትም ወደ ኔፊ ምድር መጥተ ዋልና እናም እህሎቻቸውንና ብዙ የከበሩ ነገሮቻቸውን ወስደዋልና፣ ስለዚህም እነ ርሱን አድፍጠው ጠበቁአቸው።

፳፪ እናም እንዲህ ሆነ፣ ᵐአሞንና ወንድ ሞቹ ወደ ምድሪቱ እስኪመጡ ድረስ፣ በላ ማናውያንና በሊምሂ ህዝብ መካከል ምንም ረብሻ አልነበረም።

፳፫ እናም ንጉሱ ከጠባቂው ጋር ከግንቡ ውጪ በሆነበት ጊዜ፣ አሞንንና ወንድሞቹን አገኘና፣ የኖህ ካህን ናቸው ብሎም ገመተ፣ ስለዚህ እንዲወሰዱና፣ በገመድ እንዲታሰሩ እናም ወደ ᵐወህኒ ቤት እንዲጣሉ አደረገ። እናም የኖህ ካህናት ቢሆኑ ኖሮ እንዲሞቱ ያደርግ ነበር።

፳፬ ነገር ግን እንዳልሆኑ፣ ነገር ግን የእርሱ ወንድሞች መሆናቸውን እናም ከዛራሄምላ ምድር እንደመጡ ባወቀ ጊዜ፣ እጅግ ታላቅ በሆነ ደስታ ተሞልቶ ነበር።

፳፭ አሁን ንጉስ ሊምሂ አሞን ከመም ጣቱ በፊት የዛራሄምላን ምድር ᵐእንዲፈ ልጉ ᵃአነስተኛ ቁጥር ያላቸው ሰዎችን ልኮ ነበር፣ ነገር ግን ግግኝት አልቻሉም ነበር፣ እናም በምድረበዳ ውስጥ ጠፍተው ነበር።

፳፮ ይሁን እንጂ፣ በህዝብ የነበረበት ምድር፣ አዎን፣ በደረቅ ᵐአጥንት የተሸፈነ ምድር፣ አዎን፣ በህዝብ የተሞላና የጠፉ ምድር አገኙ፤ እናም የዛራሄምላ ምድር ነው ብለው በመገመት ወደ ኔፊ ምድር ተመ ለሱ፣ ወደ ምድሪቱም ዳርቻ አሞን ከመ ምጣቱ ከጥቂት ቀናት በፊት ደረሱ።

፳፯ እናም ከእነርሱም ጋር መዝገቡን፣ እንዲሁም አጥንታቸውን ያገኙትን ህዝብ መዝገብን አመጡ፤ እናም ሰሌዳውም የተ ቀረፀው በብረት አፈር ነበር።

፳፰ እናም አሁን ሊምሂ የተቀረፁትን ለመተርጎም ንጉስ ሞዛያ ᵐከእግዚአብሔር ስጦታ እንዳለው ከአሞን አንደበት በማወቁ በድጋሚ ተደሰተ፤ አዎን፣ እናም አሞን ደግሞ ተደሰተ።

፳፱ ይሁን እንጂ ብዙዎች ወንድሞቻቸው ስለተገደሉባቸው አሞንና ወንድሞቹ በሃዘን ተሞልተው ነበር።

፴ እናም ደግሞ ንጉስ ኖህና ካህናቱ ህዝቡ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢያትና ክፋት እን ዲፈፅም አድርገው ነበር፤ ደግሞም ᵐበአ ቢናዲ ሞት አዘኑ፤ እናም ደግሞ በአልማና በእግዚአብሔር ኃይልና ጥንካሬ እናም አቢናዲ በተናገረው ቃል ባላቸው እምነት የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን በመሰረ ቱት ሰዎች ᵃመሄድ አለቀሱ።

፴፩ አዎን፣ ወዴት እንደሸሹ አላወቁምና ለሽሽታቸው አለቀሱ። አሁን እራሳቸውም ከእግዚአብሔር ጋር እርሱን ለማገልገልና

፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. ባል የሞተባት።
ለ ሞዛያ ፬፡፲፯፣ ፳፯።
፳ ሀ ሞዛያ ፳፡፳።
፳፪ ሀ ሞዛያ ፯፡፯–፲፫።
፳፫ ሀ ሞዛያ ፯፡፲፡።
ለ ሞዛያ ፯፡፲፡።
፳፭ ሀ ሔለ. ፭፡፳፭።
፳፮ ሀ ሞዛያ ፯፡፲፬።
ለ ሞዛያ ፳፡፯።
፳፯ ሀ ሞዛያ ፳፡፳።
፳፰ ሀ ኦምኒ ፩፡፳–፳፪፣
ሞዛያ ፳፰፡፲፩–፲፯።
፴ ሀ ሞዛያ ፲፯፡፲፪–፳።
ለ ሞዛያ ፲፰፡፴፬–፴፭።

ትዕዛዛቱን ለመጠበቅ ቃል ኪዳን ስለገቡ፣ ከእነርሱ ጋር በደስታ ይቀላቀሉ ነበር።

፴፪ እናም አሁን አሞን ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ ንጉስ ሊምሂ፣ እናም ደግሞ ብዙዎች ህዝቦቹ እርሱን ለማገልገልና ትዕዛዛቱን ለመጠበቅ ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን ገብተዋል።

፴፫ እናም እንዲህ ሆነ ንጉስ ሊምሂና ብዙዎች ህዝቦቹ ለመጠመቅ ፈለጉ፤ ነገር ግን በምድሪቱ [a]ከእግዚአብሔር ስልጣን የተሰጠው አንድም አልነበረም። እናም አሞን ይህን ነገር እራሱን ብቁ አገልጋይ አይደለሁም በማለት ለመፈፀም አልፈቀደም።

፴፬ ስለዚህ የጌታን መንፈስ በመጠበቅ፣ በዚያን ጊዜ ለራሳቸው ቤተክርስቲያን አላቋቋሙም ነበር። አሁን ወደ ምድረበዳው እንደሸሹት እንደ አልማና እንደ ወንድሙ መሆን ፈልገው ነበር።

፴፭ በፍፁም ልባቸው እግዚአብሔርን ለማገልገል ፈቃደኛ እንደሆኑ እንደምስክር እና አማኝ ለመጠመቅ ፈለጉ፣ ይሁን እንጂ ጊዜአቸውን አራዘሙ፣ የጥምቀታቸው ታሪክ ከዚህ ቀጥሎ [b]ይቀርባል።

፴፮ እናም አሁን የአሞንና የህዝቡ እናም የንጉስ ሊምሂና የህዝቡ ዕቅድ እራሳቸውን ከላማናውያን እጅና ከባርነት ማስለቀቅ ነበር።

ምዕራፍ ፳፩

ህዝቡ ከላማናውያን ባርነት እንዲያመልጡ እቅዱ ታቀደ—ላማናውያን እንዲሰክሩ ተደረገ—ህዝቡ አመለጡ፣ ወደ ዛራሔምላ ተመለሱ፣ እናም በንጉስ ሞዛያ አገዛዝ ስር ሆኑ። ከ፲፳፩–፲፳ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም አሁን እንዲህ ሆነ አሞንና ንጉስ ሊምሂ ህዝቡን ከባርነት እንዴት እንደሚ ያስለቅቁ መመካከር ጀመሩ፤ እናም ህዝቡ ሁሉ እንኳ በአንድነት እንዲሰበሰቡ አደረጉ፤ እናም ይህንን ያደረጉት ሁኔታውን በተመለከተ የህዝቡን ድምፅ ለመስማት ነበር።

፪ እናም እንዲህ ሆነ፤ ሴቶቻቸውንና ልጆቻቸውን፣ እናም ከብቶቻቸውን፣ መንጋዎቻቸውንና፣ ድንኳናቸውን ወስደው ወደ ምድረበዳው ከመሸሽ በስተቀር እራሳቸውን ከባርነት የሚያስለቅቁበት ምንም መንገድ ለማግኘት አልቻሉም፤ ከባርነት በጎራዴ ለመላቀቅ ቢያስቡም ላማናውያን በቁጥር ብዙ በመሆናቸው የሊምሂ ህዝብ ከእነርሱ ጋር ለመጣላት የማይቻላቸው ነበር።

፫ አሁን እንዲህ ሆነ ጌዴዎን ሔደና፣ በንጉሱ ፊት ቆመ፣ እናም እንዲህ አለው፥ አሁን ንጉስ ሆይ ከወንድሞቻችን ከላማናውያን ጋር ስንጣላ እስካሁን ብዙ ጊዜ ቃላቴን ሰምተሀልና።

፬ እናም አሁን ንጉስ ሆይ እኔ የማልጠቅም አገልጋይ ሆኜ ካላገኘኸኝ ወይም በማንኛውም ደረጃ እስካሁን ቃሌን ካዳመጥህና ለእናንተም ጠቃሚ ከሆኑ፣ እንዲሁም በዚህ ጊዜ አንተም ቃሌን እንድትሰማኝ እፈልጋለሁ፣ እናም የአንተ አገልጋይ እሆናለሁ፣ ይህንንም ህዝብ ከባርነት አላቅቃለሁ።

፭ እናም ንጉሱ ይናገር ዘንድ ፈቀደለት። ጌዴዎንም እንዲህ አለው፥

፮ የኋለኛውን መተላለፊያ፣ በኋለኛው ግንብ በኩል፣ በከተማው በስተኋላ በኩል ተመልከት። ላማናውያን፣ ወይም የላማናውያን ጠባቂዎች በምሽት ይሰክራሉ፣ ስለዚህ በእነዚህ ህዝቦች መካከል ከብቶቻቸውንና መንጋዎቻቸውን በአንድ ላይ በመሰብሰብ ወደ ምድረበዳው እንዲሸሹ አዋጅ እንላክ።

፯ እናም በትዕዛዝህ መሰረት ሄጄ የመጨረሻውን የወይን ግብር ለላማናውያን እከፍላለሁ፣ እነርሱም ይሰክራሉ፤ እናም እነርሱ ሲሰክሩና ሲተኙ በጦር ሠፈሩ በስተግራ ባለው በሚስጥር ማለፊያው እናልፋለን።

፰ ከሴቶቻችንና ከልጆቻችን፣ ከከብቶቻችንና ከመንጋዎቻችን ጋር ወደ ምድረበዳ

[a] ሀ ቅ.መ.መ. ስልጣን።
[b] ሀ ሞዛያ ፳፭፡ ፲፯–፲፰።

እንሸሻለን፤ እናም በሼምሎን ምድር አካ ባቢ እንጓዛለን።

፱ እናም እንዲህ ሆነ ንጉሱ የጌዴዎንን ቃል አዳመጠ።

፲ እናም ንጉስ ሊምሂ ህዝቡ መንጋዎቹን በአንድነት እንዲሰበስቡ አደረገ፤ እናም የወይኑን ግብር ለላማናውያን ላከ፤ ደግ ሞም እንደስጦታ ብዙ ወይን ላከላቸው፣ እናም ንጉስ ሊምሂ የላካቸውን ወይን በብ ዛት ጠጡ።

፲፩ እናም እንዲህ ሆነ የንጉስ ሊምሂ ህዝብ ከከብቶቻቸውና ከመንጋዎቻቸው ጋር በም ሽት ወደ ምድረበዳው ሸሹ፤ እናም በምድ ረበዳ ውስጥ በሼምሎን ምድር ዙሪያ ሄዱና፣ በአሞንና በወንድሞቹ በመመራት አቅጣ ጫቸውን ወደ ዛራሔምላ ምድር አደረጉ።

፲፪ እናም ወርቃቸውንና ብራቸውንና የከበሩ ነገሮቻቸውን መሸከም የሚችሉ ትን ያህል፣ ደግሞም ስንቆቻቸውን ሁሉ ወደ ምድረበዳው ወሰዱ፤ እናም ጉዞአቸ ውን ቀጠሉ።

፲፫ እናም በምድረበዳ ውስጥ ብዙ ቀናት ካደረጉ በኋላ፣ በዛራሔምላ ምድር ደረሱ፣ እናም የሞዛያ ህዝብ አባል ሆኑ፣ እንዲሁም በአገዛዙ ስር ሆኑ።

፲፬ እናም እንዲህ ሆነ ሞዛያ በደስታ ተቀ በላቸው፤ እናም ደግሞ [ሀ]መዝገባቸውንና ደግሞ በሊምሂ ህዝብ የተገኙትን [ለ]መዝገ ቦች ተቀበለ።

፲፭ እናም አሁን እንዲህ ሆነ የሊምሂ ህዝብ በምሽት መሸሻቸውን ላማናውያን ባወቁ ጊዜ፣ እነርሱን እንዲከተሉ ወታደ ሮችን ወደ ምድረበዳው ላኩ፤

፲፮ እናም ለሁለት ቀናት ከተከታተሉአ ቸው በኋላ፣ ዱካቸውን መከተል አልቻ ሉም፤ ስለዚህ በምድረበዳ ውስጥ ተሰወሩ።

በንጉስ ኖህ ህዝብ ወደ ምድረበዳ እንዲሰ ደዱ የተደረጉት የአልማና የጌታ የሆኑት ሰዎች ታሪክ።

ከምዕራፍ ፳፫ እስከ ምዕራፍ ፳፬ አጠቃሎ የያዘ።

ምዕራፍ ፳፫

አልማ ንጉስ መሆንን አልተቀበ ለም—እንደ ሊቀ ካህን አገለገለ—ጌታ ህዝቡን ገሰጸ፣ እናም ላማናውያን የሔላ ምን ምድር አሸነፉ—የንጉስ ኖህ የክፉዎቹ ካህናት አለቃ የሆነው አሙሎን፣ በላማና ውያን አገዛዝ ስር ገዛ። ከ፲፯፳–፲፳፭ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እንግዲህ አልማ የንጉስ ኖህ ወታደሮች በእነርሱ ላይ እንደሚመጡ ከጌታ ማስጠ ንቀቂያ በማግኘቱ፣ እናም ህዝቡ እንዲያ ውቀው በማድረጉ፣ ስለዚህ መንጋዎቻ ቸውን በአንድነት ሰበሰቡና፣ እህላቸውን ወሰዱ፣ እናም ከንጉስ ኖህ ወታደሮች ፊት ወደ ምድረበዳው ሸሹ።

፪ እናም የንጉስ ኖህ ህዝብ እነርሱን ለማ ጥፋት ሊደርሱባቸው እንዳይችሉ ጌታ አበ ረታታቸው።

፫ እናም በስምንት ቀን ጉዞ ወደ ምድ ረበዳው ተሰደዱ።

፬ እናም ወደ ምድሩ ደረሱ፣ አዎን፣ በጣም ቆንጆና መልካም ምድር የንፁህ ውሃ ምድር ወደሆነች መጡ።

፭ እናም ድንኳናቸውን ተከሉና፣ ምድ ሪቱን ማረስ ጀመሩ፣ እናም ህንፃን መገን ባት ጀመሩ፣ አዎን፣ ትጉህ ነበሩም፣ እጅግ ሰሩም።

፮ እናም አልማ በህዝቡ በመወደዱ የእነ ርሱ ንጉስ እንዲሆን ፈለጉ።

፯ ነገር ግን እርሱ እንዲህ አላቸው፥ እነሆ፣ ንጉስ ይኖረን ዘንድ አስፈላጊ አይ ደለም፤ ምክንያቱም ጌታ እንዲህ ብሏል፥ እናንተ አንዱን ሰው ከሌላው [ሀ]አታስበ ልጡ፣ ወይም ማንም እራሱን ከሌላው በላይ ከፍ አያድርግ፣ ስለዚህ እንዲህ እላችኋለሁ ንጉስ እንዲኖራችሁ አስፈላጊ አይደለም።

፰ ይሁን እንጂ፣ የሚቻል ከሆነ ሁልጊዜ

፡ድቅ ሰው የእናንተ ንጉስ ሊሆን ቢችል ንጉስ ለእናንተ መኖሩ መልካም ይሆናል።

፱ ነገር ግን የንጉስ ኖህንና የእርሱን ካህ ናት ᵐክፋት አስታውሱ፣ እናም እኔ ራሴም በወጥመድ ᵃተይዜ ነበርና፣ በጌታ አመለ ካከት ርኩስ የሆኑ በብርቱ ንስሃ እንድገባ የሚያደርጉኝን ብዙ ነገሮች ፈፅሜአለሁ፤

፲ ይሁን እንጂ፣ ከብዙ ᵐመከራና ችግር በኋላ፣ ጌታ ጩኸቴን ሰማና፣ ለፀሎቴ መል ስን ሰጠኝ፣ እናም ᵃብዙዎቻችሁ የእርሱን እውነታ እንድታውቁ እኔን መሳሪያው አደ ረገኝ።

፲፩ ይሁን እንጂ፣ በዚህ አልኮራም ለመ ኩራት ብቁም አይደለሁምና።

፲፪ እናም አሁን በንጉስ ኖህ ተጨቁናች ኋል፣ እናም በእርሱና በካህናቱ ባርነት ስር ሆናችኋል፣ በእነርሱም ወደ ጥፋት ተወስ ዳችኋል እላለሁ፤ ስለዚህ በኃጢያት ᵐእስ ራት ታስራችሁ ነበር።

፲፫ እናም አሁን ከዚህ ሰንሰለት በእግዚ አብሔር ኃይል ተለቅቃችኋል፤ አዎን፣ ከንጉስ ኖህና ከህዝቡ እጅ እንኳን፣ እናም ደግሞ ከክፋት ሰንሰለት ነፃ እንደወጣችሁ፣ እንዲሁም በእዚህ ᵐነፃነት ᵃፀንታችሁ እን ድትቆሙ ደግሞ እፈልጋለሁ፣ እናም ᵃማንም ሰው በእናንተ ላይ ገዢ እንዲሆን አትፍቀዱ።

፲፬ እናም ደግሞ የእግዚአብሔር ሰው ሆኖ በእርሱ ጎዳና የሚራመድና ትዕዛዛ ቱን የሚጠብቅ ካልሆነ በቀር ማንም የእ ናንተ ᵐመምህርም ሆነ አገልጋይ እንዲሆን አትፍቀዱ።

፲፭ ማንም ሰው ᵐጎረቤቱን እንደራሱ አድ ርጎ እንዲወድ፣ በመካከላቸውም ምንም ᵃፀብ እንዳይኖር አልማ ህዝቡን እንዲህ አስተማረ።

፲፮ እናም አሁን፣ አልማ ᵐሊቀ ካህንና የቤተክርስቲያናቸውም መስራች ነበር።

፲፯ እናም እንዲህ ሆነ በእርሱ በኩል ከእ ግዚአብሔር ካልሆነ በቀር ማንም ለመስበ ክም ሆነ ለማስተማር ᵐስልጣንን አልተቀበ ለም ነበር። ስለዚህ ሁሉንም የእነርሱን ካህ ናትንና መምህራኖቻቸውን ᵐመ፤ እናም ማንም ትክክለኛ ሰው ካልሆነ በቀር አል ተᵐመም ነበር።

፲፰ ስለዚህ ህዝባቸውን ጠበቁ፣ እናም ከፅ ድቅነት ጋር የተገናኙ ነገሮችን ᵐመገቧቸው።

፲፱ እናም እንዲህ ሆነ በምድሪቱ እጅግ መበልፀግ ጀመሩ፤ እናም ምድሪቱን ሌላም ብለው ጠሯት።

፳ እናም እንዲህ ሆነ በሌላም ምድር ተባዙ እጅግም በለፀጉ፤ እናም የሌላም ከተማ ብለው የሰየሟትን ከተማ ቆረቆሩ።

፳፩ ይሁን እንጂ ጌታ ህዝቡን ᵐመግሰፅ ተገቢ መሆኑን አየ፣ አዎን፣ ᵃትዕግስታቸ ውንና እምነታቸውን ፈተነ።

፳፪ ይሁን እንጂ—ᵐእምነቱን በእርሱ ያደ ረገ በመጨረሻው ቀን ᵃከፍ ይላል። አዎን እናም ለዚህ ህዝብም እንደዚህ ነበር።

፳፫ እነሆም ወደ ባርነት እንደመጡ አሳያ ችኋለሁ፤ እናም ጌታ አምላካቸው፣ አዎን የአብርሃምና የይስሐቅ እናም የያዕቆብ አም ላክ፣ ካልሆነ በቀር ማንም ሊያድናቸው አይቻለውም።

፳፬ እናም እንዲህ ሆነ፣ እርሱ አዳናቸው፣ ታላቁን ኃይሉንም አሳያቸው፣ እናም ደስ ታቸው ታላቅ ነበር።

፳፭ እነሆም፣ እንዲህ ሆነ በሌላም ምድር በነበሩበት ጊዜ፣ አዎን፣ በሌላም ከተማ፣ በዙሪያው ያለውን መሬት በሚያርሱበት ጊዜ፣ እነሆ የላማናውያን ወታደሮች በም ድሪቱ ዳርቻ ነበሩ።

፱ *ሀ* ምሳ. ፲፯፡፲፪፤
ሞዛያ ፲፭፡፭–፲፭።
ለ ሞዛያ ፲፣፡፭–፱።
፲ *ሀ* ት. እና ቃ. ፶፰፡፱።
ለ ሞዛያ ፲፰፡ ፴፰።
፲፪ *ሀ* ፪ ኔፊ ፳፰፡ ፲፱–፳፪።
፲፫ *ሀ* ቅ.መ.መ. መብት።
ለ ገላ. ፭፡፩።
ሐ ሞዛያ ፳፱፡ ፲፫።
፲፬ *ሀ* ሞዛያ ፲፰፡ ፲፰–፳፪።
፲፭ *ሀ* ቅ.መ.መ. ፍቅር።
ለ ፫ ኔፊ ፲፭፡ ፳፰–፳፱።
፲፯ *ሀ* ሞዛያ ፳፯፡ ፯።
፲፰ *ሀ* ቅ.መ.መ. ስልጣን፤
ክህነት።
፲፰ *ሀ* ፩ ጢሞ. ፪፡ ፯።
፳፩ *ሀ* ሔለ. ፲፪፡ ፫፤
ት. እና ቃ. ፶፰፡ ፳፩።
ቅ.መ.መ. መገሰጽ፣ ተግሳጽ።
ለ ቅ.መ.መ. ትዕግስት።
፳፪ *ሀ* ቅ.መ.መ. መታመን።
ለ ፩ ኔፊ ፲፫፡ ፴፯።

፳፭ አሁን እንዲህ ሆነ የአልማ ወንድሞች ከእርሻቸው ሸሹ፣ እናም በሔላም ከተማ እራሳቸውን በአንድ ላይ ሰበሰቡ፤ እናም በላማናውያን አቋም እጅግ ፈርተው ነበር።

፳፮ ነገር ግን አልማ ወደፊት ሔደና ከእ ነርሱ ጋር ቆመ፣ እናም እንዳይፈሩ፣ ነገር ግን ጌታ አምላካቸው ማስታወስ እንዳለ ባቸውና እርሱ እንደሚያድናቸው አበረ ታታቸው።

፳፯ ስለዚህ ፍርሃታቸውን ዋጡት፣ እናም እነርሱንና ሚስቶቻቸውን፣ እናም ልጆቻ ቸውን ያተርፉላቸው ዘንድ የላማናውያንን ልብ እንዲያራራ ወደ ጌታ መጮኽ ጀመሩ።

፳፱ እናም እንዲህ ሆነ ጌታ የላማናውያ ንን ልብ አራራ። እናም አልማና ወንድ ሞቹ ወደ እነርሱ ሔዱና፣ እራሳቸውን አሳልፈው ሰጡአቸው፤ እናም ላማናው ያን የሔላምን ምድር ያዙ።

፴ አሁን ከንጉስ ሊምሂ በኋላ የሚሄዱት ላማናውያን ወታደሮች ለብዙ ቀናት በም ድረበዳው ተሰወሩ።

፴፩ እናም እነሆ፣ የንጉስ ኖህን ካህናት አሙሎን በተባለ ስፍራ አገኙአቸው፤ እናም የአሙሎንን ምድር የራሳቸው አደ ረጉ፣ ምድሪቱንም ማረስ ጀመሩ።

፴፪ አሁን የካህናቱ መሪ ስም አሙሎን ነበር።

፴፫ እናም እንዲህ ሆነ አሙሎን ላማና ውያንን ተማፀነ፣ እናም ደግሞ "የላማናው ያን ሴት ልጆች የሆኑትን ሚስቶቻቸውን፣ ባሎቻቸውን እንዳያጠፉባቸው ከወንድሞ ቻቸው ጋር እንዲማፀኑ ላከ።

፴፬ እናም ላማናውያን በሚስቶቻቸው ምክንያት ለአሙሎንና ለወንድሞቹ "ርህ ራሄ ነበራቸው፣ እናም አላጠፉአቸውም።

፴፭ እናም አሙሎንና ወንድሞቹ ከላ ማናውያን ጋር አንድ ሆኑና፣ የኔፊን ምድር ለመፈለግ በተጓዙበት ወቅት በአ ልማና በወንድሞቹ የተያዘውን የሔላምን ምድር አገኙ።

፴፮ እናም እንዲህ ሆነ ወደ ኔፊ ምድር የሚወስደውን መንገድ የሚያሳዩአቸው ከሆነ ህይወታቸውንና ነፃነታቸውን እንደ ሚሰጡአቸው ላማናውያን ለአልማና ለወ ንድሞቹ ቃል ገቡ።

፴፯ ነገር ግን አልማ ወደ ኔፊ ምድር የሚ ወስደውን መንገድ ካሳያቸው በኋላ ላማና ውያን ቃላቸውን አልጠበቁም፤ ነገር ግን በአልማና በወንድሞቹ ላይ በሔላም ምድር ዙሪያ "ጠባቂዎች አስቀመጡ።

፴፰ እናም የተቀሩት ወደ ኔፊ ምድር ሔዱ፤ እናም ግማሾቹ ወደ ሔላም ምድር ተመለሱ፣ ደግሞም ትተዋቸው የሄዱትን ጠባቂዎቹ ሚስቶቻቸውንና ልጆቻቸውን አመጡ።

፴፱ እናም የላማናውያን ንጉስ ለአሙሎን በሔላም ምድር በነበረው ህዝቡ ላይ ንጉስና ገዢ እንዲሆን ፈቀደለት፤ ይሁን እንጂ ከላ ማናውያን ንጉስ ፈቃድ የሚቃረን ምንም ነገር የማድረግ ስልጣን አይኖረውም።

ምዕራፍ ፳፬

አሙሎን አልማንና ህዝቡን አሳደደ—የሚፀልዩ ከሆነ ይገደላሉ—ጌታ ሸክማቸ ውን ቀሊል እንዲመስል አደረገው—ከባ ርነት አዳናቸው፣ እናም ወደ ዛራሔምላ ተመለሱ። ከ፲፯፳፫–፲፳ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ አሙሎን በላማና ውያን ንጉስ ፊት ሞገስን አገኘ፤ ስለዚህ፣ የላማናውያን ንጉስ ለእርሱና ለወንድሞቹ በህዝቡ ላይ፣ አዎን፣ በሻምሎን ምድርም ባሉት ህዝቦች ላይ ጭምር፣ እናም እንዲ ሁም በሼምሎን ምድርና በአሙሎን ምድር ላይ መምህር ሆነው እንዲሾሙ አደረጋ ቸው።

፪ ላማናውያን እነዚህን ምድር ሁሉ ወስ ደዋልና፤ ስለዚህ፣ የላማናውያን ንጉስ በእ ነዚህ ምድር ላይ ሁሉ ነገሥታትን ሾሟል።

፫ እናም አሁን የላማናውያን ንጉስ ስሙ ላማን ይባል ነበር፣ እርሱም በአባቱ ስም ይጠራ ነበር፤ ስለዚህ ንጉስ ላማን ተብሎ

ይጠራም ነበር። እናም በብዙ ህዝብ ላይ ንጉስ ነበር።

፱ እናም በህዝቡ በተያዘው ምድር ላይ ሁሉ የአሙሎንን ወንድሞች መምህር አድርጎ ሾማቸው፤ እናም የኔፊን ቋንቋ በላማና ውያን ሁሉ መካከል ማስተማር ጀመሩ።

፲ እናም አንዱ ከሌለኛው ወዳጅ የሆኑ ህዝቦች ነበሩ፤ ይሁን እንጂ እግዚአብሔርን አያውቁትም ነበር፤ የአሙሎንም ወንድሞች ጌታ አምላካቸውንም ሆነ የሙሴን ህግ በተመለከተ ምንም አላስተማሩአቸውም ነበር፤ የአቢናዲንም ቃላት አላስተማሩአቸውም ነበር፤

፲፩ ነገር ግን ታሪካቸውን መጠበቅ እንዳለባቸውና እርስ በርስ እንዲፅፉ አስተማሩአቸው።

፲፪ እናም ላማናውያን ሀብታም መሆን ጀመሩ፣ እናም እርስ በርስ የንግድ ልውውጥ በማድረግ በጣም አደጉ፣ እንዲሁም የዓለምን ጥበብ በተመለከተ ብልጥና ብልህ ህዝብ መሆን ጀመሩ፤ አዎን፣ እጅግ ብልጥ የሆኑት ሠዎች ከራሳቸው ወንድሞች በስተቀር ሁሉንም አይነት ኃጢያትና ዝርፊያ በማድረግ ይደስቱ ነበር።

፲፫ እናም አሁን እንዲህ ሆነ አሙሎን በአልማና በወንድሞቹ ላይ [ሀ]ስልጣኑን ማሳየት ጀመረ፤ እናም እርሱን ማሳደድና፣ ልጆቹ ልጆቻቸውን እንዲያሳድዱ አደረገ።

፲፬ አልማ [ለ]ከንጉሱ ካህን አንዱ መሆኑን፣ እናም የአቢናዲን ቃል ያመነውና፣ ከንጉሱም ፊት እንዲወጣ የተደረገው እርሱ እንደነበር አሙሎን ያውቅ ነበር፤ እናም ስለዚህ በእርሱ ተቆጥቶ ነበር፤ እርሱ በንጉስ ላማን አገዛዝ ስር ነበር፣ ቢሆንም በእነርሱ ላይ ስልጣኑን ተጠቅሞ ነበር፣ እናም [ሐ]ኃላፊነቱን በእነርሱ ላይ አደረገ፣ አስገባሪዎችንም በእነርሱ ላይ አደረገ።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ ስቃያቸው ታላቅ ስለ ነበር ወደ እግዚአብሔርም በኃይል መጮህ ጀመሩ።

፲፮ እናም አሙሎን ጩኸታቸውን ማቆም እንዳለባቸው አዘዘ፣ እናም እንዲጠብቁ አቸው ጠባቂዎችን በእነርሱ ላይ አደረገ፣ ይኸውም እግዚአብሔርን የሚጠራ ማንም ሰው እንዲገደል ነበር።

፲፯ እናም አልማና ህዝቡ ወደ ጌታ አምላካቸው ድምፃቸውን ከፍ አላደረጉም፣ ነገር ግን ልባቸውን ወደ እርሱ [ሀ]አፈሰሱ፤ እናም እርሱ የልባቸውን ሐሳብ ያውቅ ነበር።

፲፰ እናም እንዲህ ሆነ የጌታ ድምፅ በስቃያቸው እንዲህ በማለት መጣ፥ ራሳች ሁን አቅኑም መልካም መፅናኛ ይኑራች ሁም፤ ከእኔ ጋር የገባችሁትን ቃል ኪዳን አውቀዋለሁና፤ ከህዝቤም ጋር ቃል ኪዳን እገባለሁ እናም ከባርነት አስለቅቃቸዋለሁ።

፲፱ እናም ደግሞ በባርነት በነበራችሁ ጊዜም ቢሆን፣ በጀርባችሁም እንኳን ሊሰማችሁ እንዳይቻላችሁ፣ በትከሻችሁ ላይ ያለውን ሸክም አቃልልላችኋለሁ፤ እናም ይህንን የማደርገው ከዚህ በኋላ ለእኔ [ለ]በምስክርነት እንድትቆሙ ነው፤ እናም እኔ ጌታ እግዚአብሔር በእውነት [ሐ]በመከራቸው ጊዜ ህዝቤን እንደምጎበኝ ታውቁ ዘንድ ነው።

፲፳ እናም አሁን እንዲህ ሆነ በአልማና በወንድሞቹ ላይ የሆነው ሸክም ቀለለላቸው፣ አዎን፣ [ለ]ሸክማቸውን ማቅለል እንዲችሉ እናም በደስታና [ሀ]በትዕግስት ለጌታ ፈቃድ ተቀባይ እንዲሆኑ ጌታ [ሐ]ብርታትን ሰጥቷቸዋል።

፲፳፩ እናም እንዲህ ሆነ እምነታቸውና ትዕግስታቸው ታላቅ በመሆኑ፣ የጌታ ድምፅ በድጋሚ እንዲህ በማለት ወደ እነርሱ መጣ፥ መፅናናትም ይብዛላችሁ፣ ነገ ከባርነት አስለቅቃችኋለሁና።

፲፳፪ እናም ለአልማ እንዲህ አለው፥ ከዚህ

፳፱ ፳ ሀ ት. እና ቃ. ፲፳፭፡ ፴፱።
፱ ሀ ሞዛያ ፲፯፡ ፩–፱፣ ፳፫፡ ፱።
ለ ሞዛያ ፳፭፡ ፫–፮።
፲፪ ሀ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. ምስክር።
ለ ቅ.መ.መ. ጭንቀት።
፲፭ ሀ አልማ ፴፩፡ ፴፯፣ ፴፫፡ ፳፫።
ለ ት. እና ቃ. ፶፩፡ ፲።
ቅ.መ.መ. ትዕግስት።
ሐ ማቴ. ፲፩፡ ፳፭–፴።

ህዝብ ፊት ትሄዳለህ፣ እናም እኔ ከአንተ ጋር እሄዳለሁ፣ ይህንንም ህዝብ ᵐከባርነት አስለቅቃለሁ።

፲፭ አሁን እንዲህ ሆነ አልማና ህዝቡ መንጋዎቻቸውን እናም ደግሞ እህላቸውን በአንድነት በምሽት ሰበሰቡ፤ አዎን፣ እንዲያውም ምሽቱን ሁሉ መንጋዎቻቸውን በአንድነት ይሰበስቡ ነበር።

፲፮ እናም ጠዋት ጌታ በላማናውያን ላይ ᵐከባድ እንቅልፍን ጣለባቸው፤ አዎን፣ እናም አስገባሪዎቻቸው ሁሉ በከባድ እንቅልፍ ላይ ነበሩ።

፲፯ እናም አልማና ህዝቡ ወደ ምድረበዳው ተጓዙ፤ እናም ቀኑን በሙሉ ከተጓዙ በኋላ ድንኳናቸውን በሸለቆ ተከሉ፣ እናም በምድረበዳው ውስጥም መንገዱን አልማ ስለመራቸው ሸለቆውን አልማ ብለው ጠሩት።

፲፰ አዎን፣ እናም በአልማ ሸለቆ ᵐምስጋናቸውን ለእግዚአብሔር አበረከቱ፣ ምክንያቱም ለእነርሱ መሀሪ ነበርና፣ እናም ሸክማቸውን አቅልሎላቸዋልና ከባርነትም አስለቅቆአቸዋልና፤ በባርነት ስር ነበሩ እናም ጌታ አምላካቸው ካልሆነ በቀር ማንም ሊያ ስለቅቃቸው አይቻለውምና።

፲፱ እናም ለእግዚአብሔር ምስጋናን አቀረቡ፣ አዎን፣ ወንዶቻቸውና፣ ሴቶቻቸው ሁሉ፣ እናም መናገር የሚችሉት ልጆቻቸው ሁሉ እግዚአብሔርን በማወደስ ድምፃቸውን ከፍ አደረጉ።

፲፲ እናም አሁን ጌታ ለአልማ እንዲህ አለው፥ ላማናውያን ነቅተዋል እናም ያሳድዱቸዋልና ፍጠን፣ አንተንና ይህንን ህዝብ ከዚህ ምድር አውጣ፤ ስለዚህ ከዚህ ምድር ውጡ፣ እናም ላማናውያኖች ይህንን ህዝብ ለማሳደድ ከዚህ አልፈው እንዳ ይመጡ በዚህ ሸለቆ ውስጥ አቆማቸዋለሁ።

፲፪ እናም እንዲህ ሆነ ከሸለቆው ወጥተው ሄዱና፣ ጉዞአቸውን ወደ ምድረበዳው አደረጉ።

፲፫ እናም ለአስራ ሁለት ቀናት በምድረበዳው ከቆዩ በኋላ በዛራሔምላ ምድር ደረሱ፤ እናም ንጉስ ሞዛያ ደግሞ በደስታ ተቀበላቸው።

ምዕራፍ ፳፭

በዛራሔምላ የሙሌቅ ወገኖች ኔፋውያን ሆኑ—ስለአልማና ስለዜኒፍ ህዝብ ተማሩ—አልማ ሊምሂንና ህዝቡን ሁሉ አጠመቀ—ሞዛያ አልማ የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን እንዲያቋቁም ስልጣን ሰጠው። በ፲፯ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም አሁን ንጉስ ሞዛያ ህዝቡ ሁሉ በአንድነት እንዲሰበሰብ አደረገ።

፪ እንግዲህ ᵐየሙሌቅ ትውልድ እንደነበረው ᶣዛራሔምላ እናም ከእነርሱ ጋር ወደ ምድረበዳው እንደመጡት ህዝብ ብዛት፣ የኔፊ ልጆች የነበሩ፣ ወይንም የኔፊ ወገን የሆኑት ብዙ አልነበሩም።

፫ እናም የኔፊም ሆኑ የዛራሔምላ ህዝብ ብዛት እንደላማናውያን አልነበረም፤ አዎን፣ ብዛታቸው እንደእነርሱ ግማሹ እንኳን አልነበረም።

፬ እናም አሁን የኔፊ ህዝብ በሙሉ፣ ደግሞም የዛራሔምላም ህዝብ በአንድነት ተሰበሰቡ፣ እናም በሁለት ወገን ሆነው በአንድነት ተሰበሰቡ።

፭ እናም እንዲህ ሆነ ሞዛያ የዜኒፍን ታሪክ ለህዝቡ አነበበ፤ እንዲነበብም አደረገ፤ አዎን፤ የዛራሔምላን ምድር ለቀው ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ በድጋሚ እስከተመለሱበት ድረስ የዜኒፍን ህዝብ ታሪክ አነበበ።

፮ እናም ደግሞ የአልማንና ወንድሞቹን ታሪክ፣ የዛራሔምላን ምድር ለቀው ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ፣ እንደገናም እስከተመለሱበት ድረስ ያለውን ስቃያቸውን ሁሉ አነበበ።

፯ እናም አሁን፣ ሞዛያ ታሪኩን አንብቦ

፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. ባርነት።
፲፱ ሀ ፩ ሳሙ. ፳፯፡፲፪።
፳፩ ሀ ቅ.መ.መ. አመስጋኝ፣ ምስጋናን፣ ምስጋና መስጠት።
፳፫ ፪ ሀ ሔለ. ፮፡፲። ቅ.መ.መ. ሙሌቅ።
ለ ኦምኒ ፩፡፲፫–፲፱።

እንደጨረሰ፣ በምድሪቱ የቀሩት ህዝቦቹ በመገረምና በአድናቆት ተሞሉ።

፳ ምን ማሰብ እንዳለባቸው አላወቁም ነበርና፤ [ሀ]ከባርነት የተለቀቁትን በተመለከቱ ጊዜ እጅግ ታላቅ በሆነ ደስታ ተሞልተው ነበርና።

፳፩ እናም በድጋሚ፣ በላማናውያን የተገደሉትን ወንድሞቻቸውን ባሰቡ ጊዜ በሃዘን ተሞሉ እናም ብዙ የሐዘን እንባም አፈሰሱ።

፲ እናም እንደገና፣ ፈጣን የእግዚአብሔርን ቸርነት እናም አልማንና ወንድሞቹን ከላማናውያን እጅና ከባርነት ማውጣቱን ባሰቡ ጊዜ፣ ድምፃቸውን ከፍ አደረጉና ለእግዚአብሔር ምስጋና አቀረቡ።

፲፩ እናም በድጋሚ፣ ወንድሞቻቸው ስለሆኑት ስለላማናውያን ኃጢያትና ስለመበከላቸው ባሰቡ ጊዜ [ሀ]ስለነፍሳቸው ደህንነት [ለ]በህመምና በጭንቀት ተሞልተው ነበር።

፲፪ እናም እንዲህ ሆነ የላማናውያንን ሴቶች ለሚስትነት የወሰዱት የአሙሎንና የወንድሞቹ ልጆች፣ በአባቶቻቸው ባህርይ ተከፉ፣ እናም ከእንግዲህ በአባቶቻቸው ስም መጠራት አልፈለጉም፣ ስለዚህ የኔፋውያን ልጆች ተብለው ይጠሩ ዘንድና ኔፋውያን ተብለው ከሚጠሩት ጋር ይቆጠሩ ዘንድ የኔፊን ስም በራሳቸው ላይ ወሰዱ።

፲፫ እናም እንግዲህ የዛራሔምላ ህዝብ ሁሉ ከኔፋውያን ጋር [ሀ]ተቆጠሩ፣ እናም ይህ የሆነበት ምክንያት የኔፊ ዘር ከሆኑት በስተቀር መንግስቱ ለሌላ ባለመሰጠቱ ነበር።

፲፬ እናም አሁን እንዲህ ሆነ ሞዛያ ለህዝቡ ንግግሩንና ንባቡን እንደጨረሰ አልማም ደግሞ ለህዝቡ እንዲናገር ፈለገ።

፲፭ እናም አልማ ተናገራቸው፣ በብዛትም በአንድ ላይ በተሰበሰቡ ጊዜ፣ እናም ከአንዱ ጉባኤ ወደ ሌለኛው በጌታ ንስሃና እምነትን እየሰበከላቸው ሔደ።

፲፮ እናም የሊምሂን ህዝብና ወንድሞቹን ከባርነት የተለቀቁትን ሁሉንም ጌታ ከባርነት እንዳስለቀቃቸው እንዲያስታውሱ በጥብቅ መከራቸው።

፲፯ እናም እንዲህ ሆነ አልማ ህዝቡን ብዙ ነገሮችን ካስተማረና ንግግሩንም ከጨረሰ በኋላ፣ ንጉስ ሊምሂ መጠመቅን ፈለገ፤ እናም ህዝቡም በሙሉ ደግሞ ይጠመቁ ዘንድ ፈለጉ።

፲፰ ስለዚህ፣ አልማ ወደ ውኃው ገባ፣ እናም [ሀ]አጠመቃቸው፤ አዎን፣ ወንድሞቹን [ለ]በሞርሞን ውሃ እንዳጠመቃቸው አይነት እነርሱንም አጠመቃቸው፤ አዎን፣ ያጠመቃቸው በሙሉ የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን አባላት ሆኑ፤ እናም ይህ የሆነው በአልማ ቃል በማመናቸው የተነሳ ነው።

፲፱ እናም እንዲህ ሆነ ንጉስ ሞዛያ በዛራሔምላ ምድር ላይ ሁሉ ቤተክርስቲያንን እንዲያቋቁም ለአልማ ፈቀደለት፣ እናም በሁሉም ቤተክርስቲያን ላይ ካህናትንና መምህራንን እንዲሾም [ሀ]ስልጣንን ሰጠው።

፳ አሁን ይህ ሁሉ የተደረገበት ምክንያት ብዙውን ህዝብ በአንድ አስተማሪ ለመምራት ስለማይቻል፣ እነርሱም ሁሉ በአንድ ጉባኤ የእግዚአብሔርን ቃል መስማት ስለማይችሉ ነበር፤

፳፩ ስለዚህ ራሳቸውን ቤተክርስቲያናት ተብለው በሚጠሩ በተለያዩ ክፍሎች ሰበሰቡ፤ እያንዳንዱ ቤተክርስቲያን የራሱ ካህናትና መምህራን አለው፣ እናም እያንዳንዱ ካህን ቃሉን ከአልማ አንደበት በተቀበለው መሠረት ይሰብክ ነበር።

፳፪ እናም ስለዚህ ብዙ ቤተክርስቲያኖች ቢኖሩም ሁሉም አንድ [ሀ]ቤተክርስቲያን ነበሩ፣ አዎን፣ ይኸውም የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን፤ ከንስሃና በእግዚአብሔር እምነት በቀር በሁሉም በቤተክርስቲያናት ምንም አይሰበክም ነበር።

፳ *ሀ* ሞዛያ ፳፪፡፲፩–፲፫።
፲፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. ነፍስ—የነፍሶች ዋጋ።
ለ ሞዛያ ፳፫፡፲–፴፤
አልማ ፲፫፡፳፯።
፲፫ *ሀ* ኦምኒ ፩፡፲፱።
፲፭ *ሀ* ሞዛያ ፳፩፡፴፭።
ለ ሞዛያ ፲፭፡፳–፲፯።
፲፱ *ሀ* ቅ.መ.መ. ክህነት።
፳፪ *ሀ* ሞዛያ ፲፭፡፲፯።

፳፫ እናም አሁን በዛራሔምላ ምድር ሰባት ቤተክርስቲያናት ነበሩ። እናም እንዲህ ሆነ ማንኛውም ᵐየክርስቶስን ወይም የእግዚ አብሔርን ስም በእራሱ ለመውሰድ የፈ ለገ የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያናት አባል ይሆናል፤

፳፬ እናም እነርሱ ᵐየእግዚአብሔር ሰዎች ተብለው ተጠርተዋል። እናም ጌታ መን ፈሱን በእነርሱ ላይ አፍስሷል፣ እነርሱም ተባርከዋል፣ በምድሪቱም ላይ በለፀገዋል።

ምዕራፍ ፳፮

ብዙዎች የቤተክርስቲያኑ አባላት እምነት በሌላቸው ወደ ኃጢያት ተመሩ—አልማ የዘለዓለማዊ ሕይወት ቃል ተገብቶለ ታል—ንስሃ የሚገቡት እና የሚጠመቁ ይቅርታን ያገኛሉ—በኃጢያት ያሉት እና ኃጢአታቸውን ለአልማና ለጌታ የተ ናዘዙ የቤተክርስቲያን አባላት ይቅር ይባ ላሉ፤ አለበለዚያ ከቤተክርስቲያን አባላት ጋር አይቆጠሩም። ከ፤፳፯–፤ ም.ዓ. ገደማ።

፩ አሁን እንዲህ ሆነ የንጉስ ቢንያምን ቃል መረዳት የማይችሉ በማደግ ላይ ያሉ ትውልዶች ነበሩ፣ እነርሱም እርሱ ለዚህ ህዝብ በተናገረበት ጊዜ ትንሽ ልጆች የነ በሩ በመሆናቸው፤ እናም የአባቶቻቸውን ባህል አያምኑም ነበር።

፪ የሙታን ትንሣኤንም ሆነ የክርስቶስን መምጣት በሚመለከት የተነገረውን አያም ኑም ነበር።

፫ እናም አሁን ባለማመናቸው የእግዚአ ብሔርን ቃል ᵐሊረዱት አልቻሉም ነበር፤ ልባቸውም ጠጥሮ ነበር።

፬ እናም አይጠመቁም ነበር፣ የቤተክር ስቲያኗም አባል አይሆኑም ነበር። እናም እምነታቸውን በተመለከተ የተለዩ ነበሩ፣ ከእዚያም በኋላ እንደዚያው ሆነው ቀሩ፣ ᵐበስጋዊነታቸውና በኃጢአተኝነታቸውም ቢሆን፣ ወደ ጌታ አምላካቸው አይፀልዩም ነበርና።

፭ እናም አሁን በሞዛያ የንግስና ዘመን እንደ የእግዚአብሔር ሰዎች ግማሽ ያህል አልበዙም ነበር፣ ነገር ግን በወንድሞች መካከል ᵐጥል ምክንያት በጣም በርክተው ነበር።

፮ እንዲህ ሆነ፣ በቤተክርስቲያን ውስጥ የነበሩትን ብዙዎችን በሽንጋይ ቃላቸው አታለሉአቸው፣ እናም ብዙ ኃጢአቶችን እንዲፈፅሙ አደረጉአቸው፣ ስለዚህ በቤ ተክርስቲያኗ ውስጥ ሆነው ኃጢያትን የፈ ፀሙ፣ በቤተክርስቲያኗ ᵐመገሰፃቸው አስ ፈላጊ ነበር።

፯ እናም እንዲህ ሆነ ከካህናቱ ፊት አመ ጡአቸው፣ እናም በመምህራንም ለካህናቱ ተሰጡ፤ እናም ካህናቱ ᵐሊቀ ካህን ከሆነው ከአልማ ፊት አመጧቸው።

፰ አሁን ንጉስ ሞዛያ አልማን በቤተክር ስቲያኗ ላይ ስልጣን ሰጥቶታል።

፱ እናም እንዲህ ሆነ አልማ ስለእነርሱ አያውቅም ነበር፤ ነገር ግን በእነርሱ ላይ ብዙ ምስክሮች ነበሩ፣ አዎን፣ ህዝቡ ቆሙና ስለኃጢአታቸው በብዛት መሰከሩ።

፲ አሁን በቤተክርስቲያኑ ፊት እንደዚህ ያለ ነገር ሆኖ አያውቅም፤ ስለዚህ አልማ በመንፈሱ ይጨነቅ ነበር፤ እናም ከንጉሱ ፊት እንዲመጡ አደረገ።

፲፩ እናም ለንጉሱ አለው፥ እነሆ ብዙዎ ቹን በወንድሞቻቸው የተከሰሱትን በአንተ ፊት አምጥተናል፤ አዎን፣ እናም በተለያዩ ክፋቶች የተያዙ ናቸው። እናም ስለኃጢአ ታቸው ንስሃ አይገቡም፤ ስለዚህ እንደወን ጆላቸው ትፈርድባቸው ዘንድ በአንተ ፊት አምጥተናቸዋል።

፲፪ ነገር ግን ንጉስ ሞዛያ አልማን እንዲህ አለው፥ እነሆ፣ እኔ አልፈርድባቸውም፣

፳፫ *ሀ* ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—የክርስቶስን ስም በራሳችን ላይ መውሰድ።
፳፬ *ሀ* ቅ.መ.መ. ቃል ኪዳን።
፳፭ ፤ *ሀ* ቅ.መ.መ. ማስተዋል።
፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. ፍጥረታዊ ሰው።
፭ *ሀ* ቅ.መ.መ. ክህደት፤ ጸብ።
፮ *ሀ* አልማ ፭፡፲፯–፲፱፡፤ ፮፡፲። ቅ.መ.መ. ማስጠንቀቅ፣ ማስጠንቀቂያ።
፯ *ሀ* ሞዛያ ፳፱፡፴፪።

ስለዚህ አንተ እንድትፈርድባቸው በእጅህ
ᵐአሳልፌ አሰጥሃለሁ።
፲፫ እናም አሁን የአልማ መንፈስ በድጋሚ
ታወከ፣ እናም ምክንያቱም በእግዚአብሔር
ዐይን የተሳሳተ ነገርን እፈፅማለሁ በማለት
ስለፈራ ወደጌታ ሄዶ ይህንን በተመለከተ
ምን ማድረግ እንዳለበት ጠየቀ።
፲፬ እናም እንዲህ ሆነ ነፍሱን ሁሉ ለእግ
ዚአብሔር ካፈሰሰ በኋላ፣ የጌታ ድምፅ ወደ
እርሱ እንዲህ ሲል መጣ፥
፲፭ አልማ አንተ የተባረክ ነህ፣ እና ᵐበሞ
ርሞን ውሃ የተጠመቁት የተባረኩ ናቸው።
የእኔ አገልጋይ በሆነው በአቢናዲ ቃል ብቻ
እጅግ ᵃበማመንህ የተባረክህ ነህ።
፲፮ እናም እነሆ አንተ በተናገርካቸው
ቃላት ብቻ እጅግ ስላመኑም የተባረኩ
ናቸው።
፲፯ እናም በዚህ ህዝብ መካከል ᵐቤተክ
ርስቲያኗን በመመስረትህ አንተ የተባረክህ
ነህ፤ እናም እነርሱም ይቋቋማሉ፣ የእኔም
ሰዎች ይሆናሉ።
፲፰ አዎን፣ ስሜን ለመቀበል ፈቃደኛ
የሆነ ይህ የተባረከ ህዝብ ነው፤ ᵐበስሜም
ይጠራሉና፣ እናም እነርሱ የእኔ ናቸው።
፲፱ እናም እኔን ህጉን ስለተላለፉት
በተመለከተ ስለጠየከኝ አንተ የተባረክህ
ነህ።
፳ አንተ የእኔ አገልጋይ ነህ፤ እናም ᵐዘለ
ዓለማዊ ሕይወት ይኖርህ ዘንድ ካንተ ጋር
ቃል ኪዳን እገባለሁ፤ እናም ታገለግለኛ
ለህም፣ በስሜም ትሄዳለህ፣ እናም በጎቼን
በአንድነት ትሰበስባለህ።
፳፩ እናም ድምጼን የሰማ የእኔ ᵐበግ ይሆ
ናል፣ እናም እናንተ በቤተክርስቲያኗ ትቀ
በሉታላችሁ፤ እኔም ደግሞ እቀበለዋለሁ።
፳፪ እነሆም ይህች የእኔ ቤተክርስቲያን
ናት፣ ማንም ᵐየሚጠመቅ ንሰሃ በመግባት
ይጠመቃል፤ እናም እናንተ የተቀበላችሁት
ማንም ቢኖር በስሜ ያምናል፤ እናም እር
ሱን በነፃ ᵃይቅር እለዋለሁ።
፳፫ እኔ የዓለምን ኃጢያት ᵐበራሴ ያደ
ረግሁ ነኝና፤ እነርሱን ᵃየፈጠርኳቸው እኔ
ነኝና፤ እናም እስከመጨረሻው ለሚያምነው
በቀኜ ያለውንም ስፍራ የምሰጠው እኔ ነኝ።
፳፬ እነሆም፣ በስሜም ተጠርተዋል፤
እናም ᵐየሚያውቁኝ ከሆነም ወደ እኔ ይመ
ጣሉ፣ እናም በቀኝ እጄ በኩል ዘለዓለማዊ
ስፍራ ይኖራቸዋል።
፳፭ እናም እንዲህ ይሆናል ᵐሁለተኛው
መለከት ሲነፋ እኔን በፍፁም ᵃያላወቁ መጥ
ተው በፊቴ ይቆማሉ።
፳፮ እና ከእዚያም እኔ ጌታ አምላካቸው፣
አዳኛቸው መሆኔን ያውቃሉ፤ ነገር ግን
አይድኑም።
፳፯ እናም ከዚያ በኋላ እኔ በጭራሽ ᵐእን
ደማላውቃቸው እናዘዝላቸዋለሁ፣ እናም
ለዲያብሎስና ለመላዕክቱ ወደተዘጋጀው
ወደ ᵃዘለዓለማዊ እሳት ሓይሄዳሉ።
፳፰ ስለዚህ እንዲህም እላችኋለሁ፣ ቃሌን
ᵐየማይሰማ፣ እርሱ በቤተክርስቲያኔ አትቀ
በሉት፣ በመጨረሻውም ቀን እርሱን አል
ቀበለውምና።
፳፱ ስለዚህ እላችኋለሁ ሂዱ፣ እናም
እኔን የተላለፈ ማንኛውንም እንደፈፀመው
ᵐኃጢያት መሰረት ᵃፍረድበት፤ እናም
በእኔና በአንተ ፊት ኃጢአቱን ᵐከተናዘዘ፣

፲፪ ᴴ ት. እና ቃ. ፴፪፣ ፫፰–፴፫።
፲፭ ᴴ ሞዛያ ፲፰፣ ፴።
ᴸ ሞዛያ ፲፯፣ ፪።
ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
፲፯ ᴴ ሞዛያ ፳፭፣ ፲፱–፳፩።
፲፰ ᴴ ሞዛያ ፩፣ ፲፩፣ ፭፣ ፰።
ቅ.መ.መ. ኢየሱስ
ክርስቶስ—የክርስቶስን ስም
በራሳችን ላይ መውሰድ።
፳ ᴴ ቅ.መ.መ. መመረጥ፤
ምርጦች፤
የዘለዓለም ህይወት።
፳፩ ᴴ ቅ.መ.መ. መልካሙ እረኛ።
፳፪ ᴴ ፪ ኔፊ ፱፣ ፳፫።
ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣
መጥመቅ።
ᴸ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ስርየት፤
ይቅርታ ማድረግ።
፳፫ ᴴ ቅ.መ.መ. መድኃኒት።
ᴸ ቅ.መ.መ. መፍጠር፣
ፍጥረት።
፳፬ ᴴ ዮሐ. ፲፯፣ ፫።
፳፭ ᴴ ት. እና ቃ. ፹፰፣ ፶፱፣ ፻፱።
ᴸ ት. እና ቃ. ፫፯፣ ፹፭–፹፯።
፳፭ ᴴ ቅ.መ.መ. መልካሙ መለከት
ᴸ ማቴ. ፯፣ ፳፭–፳፫።
ᴸ ት. እና ቃ. ፫፯፣ ፶፱–፷፩።
ሐ ሉቃ. ፲፫፣ ፳፯።
፳፮ ᴴ ፪ ኔፊ ፱፣ ፴፭፣
ት. እና ቃ. ፩፣ ፲፩።
፳፱ ᴴ ቅ.መ.መ. መልስ መስጠት፣
ሂሳብ፣ ተጠያቂነት፣
ሀላፊነት።
ᴸ ቅ.መ.መ. ዳኛ፣ ፍርድ።
ሐ ፫ ኔፊ ፩፣ ፳፯።
ቅ.መ.መ. መናዘዝ።

እናም ከልቡ ᵐንስሃ ከገባ እርሱን ᵐይቅር ትለዋለህ፣ እኔም ደግሞ ይቅር እለዋለሁ።

፴ አዎን፣ እናም ህዝቤ ᵐንስሃ እንደገባው ᴬመጠን በእኔ ላይ ያደረጉትን መተላለፍ ይቅር እላቸዋለሁ።

፴፩ እናም እያንዳንዳችሁ መተላለፋች ሁን ᵐይቅር ተባባሉ፤ እውነት እላችኋለሁ ጎረቤቱ ንስሃ በሚገባበት ጊዜ የጎረቤቱን መተላለፍ ይቅር የማይል እርሱ ራሱን ወደ ኩነኔ ያመጣል።

፴፪ አሁን እልሀለሁ፣ ሂድ፣ ለኃጢአቱ ንስሃ የማይገባ እርሱ ከህዝቤ ጋር አብሮ አይቆጠርም፤ እናም ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ይህ ደንብ ይጠበቃል።

፴፫ እናም እንዲህ ሆነ አልማ ይህንን ቃል በሰማ ጊዜ፣ እንዲኖሩት፣ እና በእግዚአብሔር ትዕዛዝ መሰረት የቤተክርስቲያን ሰዎችን ይፈረድባቸው ዘንድ ጻፋቸው።

፴፬ እናም እንዲህ ሆነ አልማ ሄደና፣ እነዚያ በክፋት የተወሰዱትን በጌታ ቃል መሰረት ፈረደባቸው።

፴፭ እና ማንኛውም ለኃጢአታቸው ንስሃ የገቡ ᵐየተናዘዙ፣ እነርሱ ከቤተክርስቲያኗ ሰዎች መካከል ቆጠራቸው።

፴፮ እናም ኃጢአታቸውን ያልተናዘዙና ለክፋታቸው ንስሃ ያልገቡ፣ እነርሱ ከቤተ ክርስቲያኗ ሰዎች መካከል አልተቆጠሩም፣ ናም ስማቸውም ᵐተሰርዟል።

፴፯ እናም እንዲህ ሆነ አልማ የቤተክርስቲያኗን ጉዳዮች ሁሉ መራ፤ እናም ለቤተ ክርስቲያኑ ጉዳዮች ሰላምና ብልፅግና በድ ጋሚ እጅግ መሳካት ጀመሩ፣ በጥንቃቄም በእግዚአብሔር ፊት በመራመድ ብዙዎችን ተቀበሉ፣ ብዙዎችን አጠመቁ።

፴፰ እናም አሁን፣ በማንኛውም ትጋት በመራመድ፣ በሁሉም ነገር የጌታን ቃል በማስተማር፣ በሁሉም መከራ በመሰ ቃየት፣ የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን አባል ባልሆኑት ሁሉ በመሳደድ፣ እነዚህ ነገሮች በሙሉ አልማና በቤተክርስቲያኗ ላይ ያሉት ተከታይ አገልጋዮች ይህንን አደረጉ።

፴፱ እናም ወንድሞቻቸውን ᵐገሰፁ፤ እናም በእግዚአብሔር ያለማቋረጥ ᴬእን ዲፀልዩና ᶜበሁሉም ነገር ምስጋናን እንዲ ሰጡም በመታዘዝ፣ እያንዳንዱ እንደ ኃጥ ያቱ፣ ወይም እንደፈፀመው ኃጢአቱ መሰ ረት በእግዚአብሔር ቃል ተገስጿል።

ምዕራፍ ፳፤

ሞዛያ ስደትን ከለከለ፣ እናም እኩል ነትን አዘዘ—ትንሹ አልማና አራቱ የሞዛያ ልጆች ቤተክርስቲያኗን ለማጥ ፋት ፈለጉ—መልአክ ታያቸው፣ እናም መጥፎ ድርጊታቸውን እንዲያቆሙ አዘዛ ቸው—አልማ በድንገት ዲዳ ሆነ—ሁሉም የሰው ዘር ደህንነትን እንዲያገኝ በድጋሚ መወለድ አለበት—አልማና የሞዛያ ልጆች የደስታ ምስራች አወጁ። ከ፲–፲፪ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም አሁን እንዲህ ሆነ በቤተክርስቲ ያኗ እምነት በሌላቸው የተሰራጨው ስደት ታላቅ ሆኖ ቤተክርስቲያኗ ማጉረምረም ተጀመረ፣ እናም በቤተክርስቲያኗ ጉዳዩን በሚመለከት በከፍተኛ ሁኔታ ለመሪዎቻ ቸው አቤቱታ ማቅረብ ተጀመረ፤ አቤቱ ታቸውንም ለአልማ አቀረቡ። አልማም በንጉስ ሞዛያ ፊት ጉዳዩን አቀረበ። እናም ሞዛያ ከካህናቱ ጋር መከረበት።

፪ እናም እንዲህ ሆነ ንጉስ ሞዛያ ማንም የማያምን የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን

፳፱ *መ* ቅ.መ.መ. መጻጸት፣ ንስሀ መግባት።
ሠ ቅ.መ.መ. ይቅርታ ማድረግ።
፴ *ሀ* ሕዝ. ፴፫፡፲፩፣ ፲፭–፲፮፣ የሐዋ. ፫፡፲፱–፳፣ ሞዛያ ፳፱፡፲፱–፳።
ለ ሞሮኒ ፮፡፰።

፴፩ *ሀ* ፫ ኔፊ ፲፫፡፲፰–፲፭፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፱–፲።
፴፫ *ሀ* ቅ.መ.መ. መናዘዝ።
፴፮ *ሀ* ዘፀአ. ፴፪፡፴፣ አልማ ፭፡፳፱። ቅ.መ.መ. ውግዘት፣ የሕይወት መፅሐፍ።

፴፱ *ሀ* ቅ.መ.መ. ማስጠንቀቅ፣ ማስጠንቀቂያ።
ለ ፪ ኔፊ ፴፪፡፳–፴።
ሐ ቅ.መ.መ. አመስጋኝ፣ ምስጋናን፣ ምስጋና መስጠት።

አባል የሆኑትን ᵐማሳደድ እንደሌለበት በም ድሪቱ ዙሪያ አዋጅን አሰራጨ።

፫ እናም በቤተክርስቲያኗ ሁሉ መካከል ስደት መኖር እንደሌለበት፣ በሰዎች መካከል ᵐእኩልነት እንዲሆን ጥብቅ ትዕዛዝ ነበር፣

፬ ምንም ኩራትና ብጥበጣ ᵐሰላማቸውን ለማደፍረስ እንዲኖር አይፍቀዱ ዘንድ፤ ለራሳቸውም ድጋፍ በራሳቸው እጅ እየ ሰሩም፣ እያንዳንዱ ሰው ጎረቤቱን እንደ ራሱ ᵃያክብሩ ዘንድ ጥብቅ ትዕዛዝ ነበር።

፭ አዎን፣ እናም ካለህመም ወይም በድ ህነት ምክንያት በቀር፣ ሁሉም ካህናትና መምህራን ለራሳቸው በእጃቸው ᵐመስራት አለባቸው፤ እናም እነዚህን ነገሮች ሲያደ ርጉ ከመጠን ይልቅ በበለጠ ᵃበእግዚአብ ሔር ጸጋ ተሞሉ።

፮ እናም እንደገና በምድሪቱ ታላቅ ሠላም መስፈን ጀመረ፤ ህዝቡም ብዙ መሆን ጀመሩ፤ እናም በምድር ገፅ ባሻገርም፣ አዎን በስተሰሜንና በደቡብም፣ በምስራቅና በምዕራብ፣ ታላላቅ ከተሞችንና መንደሮ ችን በሁሉም በምድሪቱ ክፍል በመገንባት መበተን ጀመሩ።

፯ እናም ጌታ ጎበኛቸውና አበለፀጋቸው፣ እንዲሁም ታላቅና ሀብታም ህዝቦች ሆኑ።

፰ አሁን የሞዛያ ልጆች ከማያምኑት ጋር የተቆጠሩ ነበሩ፤ እናም ደግሞ በአባቱ ስም አልማ ተብሎ የተጠራው ᵐከአልማ ልጆ ችም አንዱ ከእነርሱ ጋር የተቆጠረ ነበር፤ ይሁን እንጂ፣ እርሱ እጅግ ኃጢአተኛና ᵃአመንዝራ ሰው ሆነ። እናም እርሱ በጣም ተናጋሪ ሰው ነበርና፣ ብዙ ሽንገላን ለህዝቡ ይናገር ነበር፤ ስለዚህም ብዙውን ህዝብ የእ ርሱን ክፋት እንዲከተሉ አደረገ።

፱ እናም የህዝቡን ልብ ᵐበመስረቅ፣ በህ ዝቡ መካከል ብዙ ፀብ እንዲኖር በማድ ረግ፣ የእግዚአብሔር ጠላት ስልጣኑን በእነ ርሱ ላይ እንዲያሳይ እድል በመስጠት ለእ ግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ዕድገት ታላቅ እንቅፋት ሆነ።

፲ እናም አሁን እንዲህ ሆነ የእግዚአብ ሔርን ቤተክርስቲያን ለማጥፋት ወደተለ ያዩ ᵐፍራዎች በሄደ ጊዜ፣ እናም ከእግ ዚአብሔር ትዕዛዝ ወይም ከንጉሱም እንኳን ተቃራኒ በሆነ መንገድ፣ የጌታን ህዝብ ወደ ተሳሳተው መንገድ ለመምራት ቤተክርስቲ ያንን ለማጥፋት ከሞዛያ ልጆች ጋር በሚስ ጥር ይሄድ ነበርና—

፲፩ እናም እንዳልኳችሁ ᵐበእግዚአብ ሔር ላይ በማመፅ እየሄዱ እያሉ፣ እነሆ፣ የጌታ ᵃመልአክ ᶣታያቸው፤ እናም በደ መና ውስጥ እንደነበረ ወረደ፤ የቆሙበት ንም ምድር እንዲንቀጠቀጥ በሚያደርግ ሁኔታ እንደነጎድጓድ ድምፅ ተናገረ፤

፲፪ እናም አድናቆታቸው እጅግ ታላቅ ሆኖ በመሬትም ላይ ወደቁ፣ እናም እርሱ የሚናገራቸውን ቃላት አልተረዱም ነበር።

፲፫ ይሁን እንጂ በድጋሚ እንዲህ ሲል ጮኸ፥ አልማ ተነስና፣ ቁም፣ የእግዚአብ ሔርን ቤተክርስቲያን ለምን ታሳድዳለህ? ጌታ እንዲህ ብሏልና፣ ይህች ᵐየእኔ ቤተክር ስቲያን ናት፣ እናም አቋቁማታለሁ፤ ከህዝቤ መተላለፍ በስተቀር ምንም አይሸራትም።

፲፬ እናም በድጋሚ፣ መልአኩ አለ፥ እነሆ፣ ጌታ የዚህን ህዝብ ᵐፀሎት፣ እናም ደግሞ የአባትህን የአልማን ፀሎት ሰምቷል። አንተ ወደ እውነት እውቀትም ትመጣ ዘንድ አንተን በተመለከተ በታላቅ እምነት ፀልዮ አል፤ ስለዚህ፣ ለዚህ ዓላማ የእግዚአብሔ ርን ኃይልና ስልጣን ለማሳመን፣ በእምነታ ቸው መሰረት የአገልጋዮቹ ᵃፀሎት መልስ ያገኝ ዘንድ ነው የመጣሁት።

፳፯ ፪ ᵐ ቅ.መ.መ. ማሳደድ፣ መሳደድ።
፫ ᵐ ሞዛያ ፳፫፡፲፣ ፳፱፡፴፪።
፬ ᵐ ቅ.መ.መ. ሰላም።
ᵃ ቅ.መ.መ. መቆጠር።
፭ ᵐ ሞዛያ ፲፰፡፳፡፣ ፳፯።
ᵃ ቅ.መ.መ. ጸጋ።
፰ ᵐ ቅ.መ.መ. አልማ፣ የአልማ ወንድ ልጅ።
ᵃ ቅ.መ.መ. ጣኦት አምላኪ።
፱ ᵐ ፪ ሳሙ. ፲፭፡፩–፮።
፲፩ ᵐ ቅ.መ.መ. አመጽ።
ᵃ ቅ.መ.መ. መላእክት።
ᶣ የሐዋ. ፱፡፩–፱፣ አልማ ፰፡፣ ፲፭።
፲፫ ᵐ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—የቤተክርስትያኗ ራስ።
፲፬ ᵐ አልማ ፲፡ ፳፪።
ᵃ ሞር. ፱፡ ፴፯–፴፯።

፲፭ እናም አሁን እነሆ፣ የእግዚአብሔ
ርን ኃይል መጠራጠር ትችላለህን? እነሆም
ድምፄስ ምድርን አላንቀጠቀጠምን? እናም
ከፊትህ ደግሞ እኔን ማየት አይቻልህምን?
እኔም ከእግዚአብሔር ተልኬአለሁ።

፲፮ አሁን እንዲህ እልሃለሁ፥ ሂድ፣ እናም
የአባቶችህን ምርኮ በሔላምና በኔፊ ምድር
አስታውስ፣ እናም ለእነርሱ ምን ያህል
ታላቅ ነገር እንዳደረገ አስታውስ፤ በባር
ነት ነበሩና እርሱ "አድኖአቸዋልና። እናም
አሁን አልማ እንዲህ እላለሁ፣ በመንገድህ
ሂድ፣ ራስህን ለመጣል ብትፈልግም፣ ቤተ
ክርስቲያኗን ለማጥፋት አትፈልግ፣ ምክን
ያቱም ፀሎታቸው ምላሽ ያገኛልና።

፲፯ እናም አሁን እንዲህ ሆነ እነዚህ መል
አኩ ለአልማ የተናገረው የመጨረሻ ቃላት
ነበሩ፣ እናም ሄደ።

፲፰ እናም አሁን አልማና ከእርሱ ጋር የነ
በሩት በምድር ላይ ወደቁ፣ መደነቃቸው
ታላቅ ነበርና፤ በራሳቸው ዐይንም የጌታን
መልአክ ተመልክተዋልና፤ እናም ድምፁ
ምድርን እንደሚያንቀጠቅጥ ነጎድጓድ
ነበር፣ እናም ከእግዚአብሔር ኃይል በቀር
ምንም መሬትን እንደሚከፍል አይነት ምድ
ርን ለማንቀጥቀጥ የሚችል እንደሌለ አወቁ።

፲፱ እናም አሁን የአልማ መደነቅ ታላቅ
ስለነበር ዲዳ ሆነ፣ አፉንም መክፈት አልቻ
ለም፤ አዎን፣ እና ደካማ ሆነ፣ እጁን እንኳ
ማንቀሳቀስ እስኪያቅተው፤ ስለዚህ ከእ
ርሱ ጋር በነበሩት ተወሰደና፣ በአባቱ ፊት
እስከሚወድቅ ድረስ እራሱን መርዳት አቅ
ቶት ተሸከሙት።

፳ እናም ለአባቱ በእነርሱ ላይ የሆነውን
ሁሉ ገለፁለት፣ እናም አባቱ የእግዚአብ
ሔር ኃይል መሆኑን በማወቁ ተደሰተ።

፳፩ እናም ጌታ ለልጁና ደግሞ ከእርሱ ጋር
ለነበሩት ያደረገውን ይመሰክሩ ዘንድ ብዙ
ዎች በአንድነት እንዲሰበሰቡ አደረገ።

፳፪ እናም ካህናት እራሳቸውን በአንድነት
እንዲሰበስቡ አደረገ፤ እናም የእግዚአብሔ
ርን ክብርና ቸርነት ያውቁና፣ ይመለከቱ
ዘንድ የህዝቡም ዐይን እንዲከፈት፣ ጌታ
የአልማን አንደበት ይናገርበትም ዘንድ እን
ዲከፍት፤ እናም ደግሞ እጅና እግሮቹ ብር
ታትን ያገኙ ዘንድ ወደአምላካቸው መፀለ
ይና መፆም ጀመሩ።

፳፫ እናም እንዲህ ሆነ ለሁለት ቀናትና
ሁለት ሌሊት ከፆሙና ከፀለዩ በኋላ የአ
ልማ እግሮችና እጆች ብርታትን አገኙ፣
እናም ተነስቶ መናገር ጀመረ፣ መልካም
መፅናናት እንዲሆንላቸውም ተናገረ።

፳፬ እንዲህ አለ፥ ለኃጢአቴ ንስሃ ገብቻ
ለሁ፣ እናም "በጌታ ድኔአለሁ፤ እነሆም
ከመንፈስ ተወልጃለሁ።

፳፭ እናም ጌታ አለኝ፥ ሁሉም የሰው ዘር፣
አዎን፣ ወንዶችና ሴቶች፣ ሁሉም ሀገር፣
ነገድ፣ ቋንቋና ህዝብ "በድጋሚ መወለድ
ይገባቸዋልና አትደነቅ፤ አዎን ከእግዚአ
ብሔር በመወለድ፣ ^ከስጋዊና ከወደቁ
በት ሁኔታ፣ ወደ ፃድቁ መንገድ በእግዚ
አብሔር በመዳን፣ የእርሱም ወንድና ሴት
ልጆች በመሆን ^ይለወጣሉ፤

፳፮ እናም በዚህም አዲስ ፍጡራን ይሆ
ናሉ፣ ይህንን ካላደረጉ፣ "በምንም መን
ገድ የእግዚአብሔርን መንግስት ሊወርሱ
አይችሉምና።

፳፯ እላችኋለሁ፣ ጉዳዩ ይህ ካልሆነ፣
መጣል አለባቸው፤ እናም ይህንን አውቃ
ለሁ ምክንያቱም እኔ ልጣል ነበርና።

፳፰ ይሁን እንጂ፣ በብዙ መከራ ላይ
ከተገፋሁ በኋላ ልሞት ስል፣ ንስሃ ገባሁ፣
ጌታም በምህረቱ "ከዘለዓለማዊ ቃጠሎ እን
ድወጣ አደረገኝ፣ እናም እኔ ከአምላክ ተወ
ለድኩ።

፳፱ ነፍሴ ከሞላው መራራ መርዝ፣ እና
ከክፋት ሰንሰለት ተፈወሰች። እኔም በጨ

፲፯ *ሀ* ሞዛያ ፳፫፡፭–፴።
፳፰ *ሀ* ፪ ኔፊ ፪፡፮–፯።
ቅ.መ.መ. ቤዛ፣ ማዳን፣ ቤዛነት።
፳፭ *ሀ* ሮሜ ፮፡፫–፲፩፣ ሞዛያ ፭፡፯፣ አልማ ፭፡፲፬፣ ሙሴ ፮፡፶፱። ቅ.መ.መ. ዳግመኛ መወለድን፣ ከእግዚአብሔር መወለድ።
ለ ቅ.መ.መ. ስጋዊ።
ሐ ሞዛያ ፫፡፲፱፣ ፲፯፡፫። ፳፯ *ሀ* ዮሐ. ፫፡፭። ፳፰ *ሀ* ፪ ኔፊ ፱፡፲፯።

ለማ አዘቅት ነበርኩ፤ ነገር ግን አሁን አስ ደናቂውን የአምላክ ብርሃን ተመለከትኩ። ነፍሴ ᵐበዘለአለማዊ ቅጣት ተሰቃየች፤ ነገር ግን እኔ ተነጥቄአለሁ፣ እናም ከእንግዲህ ነፍሴ ህመም የለባትም።

፴ አዳኜን አልተቀበልኩትም፣ እናም በአባቶቻችን የተነገረውን ክጄአለሁ፤ ነገር ግን አሁን እንደሚመጣ፣ እናም ጌታ የፈ ጠረውን ማንኛውንም ፍጡር እንደሚያስ ታውስ አስቀድመው እንዲመለከቱ፣ እር ሱም እራሱን ለሁሉም ይገልፃል።

፴፩ አዎን፣ ᵐሁሉም ጉልበት ይንበረ ከካል፣ እናም የሁሉም አንደበት በፊቱ ይናዘዛል። አዎን፣ እንዲሁም በመጨረ ሻው ቀንም ሁሉም ሰው በእርሱ ᵃለፍርድ በሚቆሙበት ጊዜ፣ ከዚያም እርሱ አም ላክ መሆኑን ይናዘዛሉ፤ በዓለም ላይ ᵃያለ እግዚአብሔር የሚኖሩትም የዘለአለማዊው ቅጣት በእነርሱ ላይ ትክክል መሆኑን ይና ዘዛሉም፤ ይንዘፈዘፋሉም፣ ይንቀጠቀጣ ሉም፣ እናም ሁሉም በቅጽበት ᵐበሚያ ዩት ዐይኖች ፊት ይሸማቀቃሉ።

፴፪ እናም አሁን እንዲህ ሆነ አልማ ከዚ ህን ጊዜ ጀምሮ ህዝቡን ማስተማር ጀመረ፣ እናም መልእክቱ በተገለፀላቸው በዚያን ጊዜ ከአልማ ጋር የነበሩት ስላዩትና ስለሰሙት ነገሮችም ለሁሉም ህዝብ በማወጅ፣ እናም በከፍተኛ መከራ፣ እምነት በሌላቸውም ታላቅ ስደትን እየተቀበሉ፣ በብዙዎችም እየተመቱ በምድሪቱ ዙሪያ ሁሉ እየተጓዙ የእግዚአብሔርን ቃል ሰበኩ።

፴፫ ነገር ግን ይህ ሁሉ ቢሆንም፣ እምነ ታቸውን በማረጋገጥ፣ እናም የጌታን ትዕ ዛዛት እንዲጠብቁ በትእግስት እና በብዙ ስቃይ በጥብቅ በማበረታታት ለቤተክርስ ቲያኑ ብዙ ማፅናኛ ሰጡ።

፴፬ እናም አራቱም ᵐየሞዛያ ልጆች ነበሩ፣ ስማቸውም አሞን፣ አሮን፣ ኦምነር፣ እናም ሔምኒ ነበሩ፣ እነዚህ የሞዛያ ወንድ ልጆች ስሞች ነበሩ።

፴፭ እናም በቤተክርስቲያኑ ላይ የፈፀሙ ትን በደል ሁሉ በቀናነት ለማደስ በቅንነት በመሞከር፣ ኃጢአታቸውን ሁሉ ለመናዘ ዝና፣ ያዩትን ነገሮች ሁሉ በማወጅ፣ እናም ትንቢትንና ቅዱሳን መፃህፍትን መስማት ለፈለጉ ሁሉ በመግለጽ፤ በዛራሔምላ ምድር ሁሉ፣ እናም በንጉስ ሞዛያ አገዛዝ ስር ከነበሩት ሰዎች መካከል ተጓዙ።

፴፮ እናም ብዙዎችን እውነትን እንዲ ያውቁ፣ አዎን ወደ አዳኛቸው እውቀት ለማምጣት እንደዚህም በጌታ እጅ መሳ ሪያ ነበሩ።

፴፯ እናም እነርሱ እንዴት የተባረኩ ናቸው! ሰላምን ᵐአውጀዋልና፤ መል ካም የሆነውን ᵃየምስራች ዜና አውጀዋል፤ እናም ለህዝቡም ጌታ እንደሚነግስ አው ጀዋል።

ምዕራፍ ፳፯

የሞዛያ ልጆች ላማናውያንን ሊሰብኩ ሔዱ—ሁለቱን የባለራዕይ ድንጋዮች በመጠቀም ሞዛያ የያሬዳውያንን ሰሌዳ ዎች ተረጎመ። በ፲፪ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እንግዲህ እንዲህ ሆነ ᵐየሞዛያ ልጆች እነዚህን ነገሮች ሁሉ ካደረጉ በኋላ ጥቂቶ ቹን ከእነርሱ ጋር ወሰዱ፣ እናም ወደ ንጉሱ አባታቸው ተመለሱ፤ እናም በዚህም እነ ርሱ ከመረጧቸው ጋር በመሆን፣ የሰሙአ ቸውን ነገሮች ይሰብኩ ዘንድ እናም የጌታን ቃላት ለወንድሞቻቸው ለላማናውያን ያካ ፍሉ ዘንድ ᵃወደኔፊ ምድር እንዲሄዱ እን ዲፈቅድላቸው ፈለጉ—

፪ ምናልባት ወደጌታ አምላካቸው እው

፳፱ ᵇ ሞዛያ ፪፡ ፴፯።
፴፩ ᶜ ፊልጵ. ፪፡ ፱–፲፩፤ ሞዛያ ፲፮፡ ፩–፪፤ ት. እና ቃ. ፹፯፡ ፹፩።
ᵃ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—ዳኛ።
ᵃᵃ አልማ ፵፩፡ ፲፩።
ᵐᵐ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ።
፴፪ ᵇ ቅ.መ.መ. አሞን፣ የሞዛያ ወንድ ልጅ።
፴፯ ᵇ ኢሳ. ፶፪፡ ፯፤ ሞዛያ ፲፭፡ ፲፩–፲፯። ቅ.መ.መ. መስበክ።
ᵃ ቅ.መ.መ. ወንጌል።
፳፯ ᵃ ᵇ ᵇᵇ ᵃᵃ ᵐᵐ ᵃᵃᵃ ᵐᵐᵐ ᵃᵃᵃᵃ ᵐᵐᵐᵐ ᵃᵃᵃᵃᵃ ᵐᵐᵐᵐᵐ ᵃᵃᵃᵃᵃᵃ ᵐᵐᵐᵐᵐᵐ ᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃ ᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐ ᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃ ᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐ ᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃ ᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐ ᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃ ᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐ ᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃ ᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐ ᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃ ᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐ ᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃ ᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐ ᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃ ᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐ ᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃ ᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐ ᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃ ᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐ ᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃ ᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐ ᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃ ᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐ ᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃ ᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐ ᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃ ᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐᵐ

ቀት ያመጧቸው ዘንድ፣ እናም የአባቶቻቸ
ውንም ክፋት እንዲያሳምኑአቸው፤ እናም
ምናልባት ወደኔፋውያን ካላቸው ᵐጥላቻ
ያድኗቸው ዘንድ፣ በጌታ በአምላካቸውም
ደግሞ ወደመደሰት ያመጧቸው ዘንድ፣
እርስ በራስም ወዳጅ ይሆን ዘንድ፣ እናም
ጌታ አምላካቸውም በሰጣቸው ምድር ሁሉ
ከእንግዲህ ጠብም እንዳይኖር ለማድረግ
ይችሉ ዘንድ እንዲፈቅድላቸው ፈለጉ።

፲ አሁን ደህንነት ለሁሉም ፍጡር መታ
ወጅ እንደሚገባው ፍላጎት ነበራቸው፣
የማንም የሰው ᵐነፍስ መጥፋቱን ᵃሊቀ
በሉት አልቻሉምና፤ አዎን ማንኛውም
ነፍስ ᵃᵃመጨረሻ የሌለውን ቅጣት የሚቀ
በል መሆኑ ማሰባቸውም እንዲንዘፈዘፉና
እንዲንቀጠቀጡ ያደርጋቸዋል።

፲፩ እናም የጌታ መንፈስ በእነርሱ ላይ ሰርቶ
ነበር፣ እነርሱ ᵐከሁሉም በላይ መጥፎ የሆኑ
ኃጢአተኞች ነበሩና። እናም ጌታ ማብቂያ
በሌለው ᵃምህረቱ እነርሱን ለማዳን አስፈ
ላጊ መሆኑን ተረዳ፤ ይሁን እንጂ በክፋታ
ቸው ምክንያት ብዙ የነፍስ ስቃይ ተሰቃዩ፣
እናም ለዘለዓለም እንጣላለን ብለው በመፍ
ራታቸው የተነሳ ብዙ ተሰቃዩ።

፲፪ እናም እንዲህ ሆነ ወደ ኔፊ ምድር
ይወጡ ዘንድ ከአባቶቻቸው ጋር ለብዙ
ቀናት ተማፀኑ።

፲፫ እናም ንጉስ ሞዛያ ሄደና፣ ልጆቹ ከላ
ማናውያን መካከል ሄደው ወንጌልን ለማ
ስተማር ፍቃድ እንዲሰጣቸው እንደሚገ
ባው ጌታን ጠየቀ።

፲፬ እናም ጌታ ለሞዛያ እንዲህ አለው፥
እንዲሄዱ ፍቀድላቸው፣ ብዙዎች በቃላ
ቸው ያምናሉና፣ እናም ዘለዓለማዊ ህይ
ወት ይኖራቸዋል፤ እናም እኔ ወንድ ልጆ
ቻቸሁን ከላማናውያን እጅ ᵐአድናቸዋለሁ።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ ሞዛያ በጠየቁትም
መሰረትም እንዲሄዱና ያደርጉ ዘንድ ፈቀ
ደላቸው።

፲፮ እናም በላማናውያን መካከል ቃሉን
ለመስበክ ወደ ምድረበዳ ᵐሄዱ፣ እናም
ከዚህ በኋላ የታሪካቸውን ᵃዘገባ እሰጣለሁ።

፲፯ አሁን ንጉስ ሞዛያ መንግስቱን የሚሰ
ጥበት ማንም አልነበረውም፣ ምክንያቱም
ከልጆቹም ማንም መንግስቱን የተቀበለ
አልነበረም።

፲፰ ስለዚህ እናም ለንጉስ ሞዛያ በሊምሂ
እጅ የተሰጡትን በሊምሂ ህዝብ የተገኙትን
ᵐወርቃማ ሠሌዳዎች ከተረጎመና በመዝ
ገብ እንዲፃፍ ካደረገ በኋላ፣ ᵃበነሃስ ሰሌ
ዳና፣ ደግሞም በኔፊ ሠሌዳዎች ላይ የተቀ
ረፁትንና፣ ሁሉንም በእግዚአብሔር ትዕ
ዛዝ መሰረት የተቀመጡትን እና የተጠበቁ
ትን ነገሮች ወሰደ፤

፲፱ እናም ይህን ያደረገው በህዝቡ ታላቅ
ጉጉት የተነሳ ነው፣ ምክንያቱም እነርሱ
ስለጠፉት ሰዎች ለማወቅ ፍላጎታቸው
ከልክ በላይ ነበርና።

፲፲ እናም አሁን በሁለቱ የቀስት ጫፎች
ላይ በታሰሩት ᵐድንጋዮች አማካኝነት ተረ
ጎማቸው።

፲፳ አሁን እነዚህ ነገሮች ከመጀመሪያው
ጀምሮ ተዘጋጅተዋል፣ እናም ቋንቋዎችን
ለመተርጎም አላማም ከትውልድ ወደ ትው
ልድ ተላልፈዋል፤

፲፳፩ እናም የምድሪቱን ሰዎች ክፋትና እር
ኩሰት ማንኛውም ፍጡር ያገኘው ዘንድ፣
በጌታ እጅ ተጠብቀዋል፣ እናም ተቀምጠ
ዋል፤

፲፳፪ እናም እነዚህን ነገሮች ያሏቸው ሁሉ
እንደጥንት ጊዜ አይነት ᵐባለራዕይ ይባላሉ።

፲፳፫ አሁን ሞዛያ እነዚህን ታሪኮች ተርጉሞ

፪ ሀ ያዕቆ. ፯፡፳፪።
፲ ሀ ቅ.መ.መ. ነፍስ—
የነፍሶች ዋጋ።
ለ አልማ ፲፫፡፳፯፤
፲ ኔፊ ፲፯፡፲፡፤
ሙሴ ፯፡፱–፲፤
ሐ ያዕቆ. ፯፡፲፤
ት. እና ቃ. ፲፱፡፣–፲፪።
፲፩ ሀ ሞዛያ ፳፯፡፣።
ለ ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።
፲፯ ሀ አልማ ፲፱፡፳፪–፳፫።
፲፱ ሀ አልማ ፲፯፡፯–፱።
ለ አልማ ፲፯–፳፭።
፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. የወርቅ ሰሌዳዎች።
ለ ቅ.መ.መ. የነሀስ ሰሌዳዎች።
፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. ኡሪም እና
ቱሚም።
፲፯ ሀ ሞዛያ ፳፡፲፫–፲፳።
ቅ.መ.መ. ባለራዕይ።

ከጨረሰ በኋላ፣ እነሆ፣ [ሀ]የጠፉትን ህዝቦች ከጠፉበት ጊዜ አንስቶ [ለ]ታላቁ ግንብ እስ ከተገነባበት፣ ጌታ የህዝቡን ቋንቋ [ሐ]በቀለ ቀለበት ጊዜ እናም በምድር ገፅ ሁሉ እስከ ተበተኑበት፤ አዎን፣ እናም ከጥንት አዳም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን ጭምር የህዝቡን ታሪክ ሰጠ።

፲፫ አሁን ይህ ታሪክ የሞዛያ ህዝብ እጅግ እንዲያለቅስ አደረገ፤ አዎን በሀዘን ተሞ ልተው ነበር፣ ይሁን እንጂ ብዙ እውቀ ትን ሰጥቷቸዋል፣ በእርሱም ተደስተዋል።

፲፬ እናም ይህ ታሪክ ከዚህ በኋላ ይፃፋል፣ እነሆም፣ በዚህ መዝገብ የተፃፉትን ነገሮች ሁሉም ሰው ማወቁ አስፈላጊ ነውና።

፲፭ እናም አሁን፣ እኔ እንዳልኳችሁ፣ ንጉስ ሞዛያ እነዚህን ነገሮች ካደረገ በኋላ [ሀ]የነሃስ ሰሌዳዎቹን፣ እናም ያስቀመጣቸ ውን ሁሉንም ነገሮች ወሰደና፣ የአልማ ልጅ ለሆነው ለአልማ ሰጠው፤ አዎን፣ ሁሉንም መዛግብትና፣ ደግሞ [ለ]መተርጎሚያውን፣ እናም ሁሉንም ለእርሱ ሰጠ፣ እንዲጠብ ቃቸውና [ሐ]እንዲያስቀምጣቸው፣ ደግሞም የህዝቡን ታሪክ እንዲያስቀምጥ፣ ልክ ሌሂ ኢየሩሳሌምን ለቆ ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ እንደተላለፈው፣ ከአንዱ ትውልድ ወደ ሌላኛው እንዲያስተላልፍ አዘዘው።

ምዕራፍ ፳፱

ሞዛያ በንጉስ ቦታ ዳኛዎች እንዲመ ረጡ ሀሳብ አቀረበ—ፃድቃን ያልሆኑ ንጉሶች ህዝባቸውን ወደኃጢያት ይመ ራሉ—ትንሹ አልማ ዋና ዳኛ እንዲ ሆን በህዝቡ ድምፅ ተመረጠ—እርሱም ደግሞ በቤተክርስቲያኗ ላይ ሊቀ ካህን ነው—አልማ ትልቁና ሞዛያ ሞቱ። ከ፣ቀ–፣ቀ ም.ዓ. ገደማ።

፩ አሁን ሞዛያ ይህንን ሲያደርግ ንጉሳ ቸው ማን መሆን እንዳለበት ፈቃዳቸውን በተመለከተ ለማወቅ በህዝቡ ሁሉ መካከል በምድሪቱ ዙሪያ ላከ።

፪ እናም እንዲህ ሆነ የህዝቡ ድምፅ እን ዲህ ሲል መጣ፥ የአንተ ልጅ አሮን ንጉሳ ችን እና ገዢአችን እንዲሆን እንፈልጋለን።

፫ አሁን አሮን ወደ ኔፊ ምድር ተጉዟል፣ ስለዚህ ንጉሱ መንግስቱን ለእርሱ ሊሰጠው አልተቻለውም፤ አሮንም በራሱ ላይ መንግ ስትን አይቀበለም፣ ወይም ማንም [ሀ]የሞዛያ ልጆች የሆኑ መንግስቱን በራሱ ላይ ለማድ ረግ አልፈቀደም።

፬ ስለዚህ ንጉስ ሞዛያ በህዝቡ መካከል በድጋሚ ላከ፤ አዎን፣ እንዲሁም የፅሁፍ መልዕክትን በህዝቡ መካከል ላከ። እናም እነዚህም የተፃፉትም ቃላት እንዲህ የሚሉ ነበሩ፥

፭ እነሆ፣ አቤቱ እናንተ ህዝቦቼ ሆይ፣ ወይም ወንድሞቼ፣ እኔ እንደዚህ በጣም አከብራችኋለሁና፣ እኔ እንድታስቡበት የሚፈለግባችሁን ጉዳይ እንድታስቡበት እፈልጋለሁ—[ሀ]ንጉስ እንዲኖራችሁ ፈል ጋችኋልና።

፮ አሁን መንግስቱ በትክክል የሚገባው እንዳልተቀበለው፣ እናም መንግስቱንም በራሱ ላይ እንደማይወስድ እነግራችኋለሁ።

፯ እናም አሁን በእርሱ ምትክ ሌላ የሚ ሾም መኖር ካለበት፣ እነሆ በእናንተ መካ ከል ጠብ እንዳይነሳ እፈራለሁ። እናም ምናልባት የእኔ ልጅ መንግስቱ የሚገባው ተቆጥቶና የህዝቡን ግማሽ ከእርሱ ጋር ይወ ስድ ይሆናል፣ ይህም ከእናንተ ጋር ጦርነ ትና ፀብን ይፈጥራል፣ ያውም ለብዙ ደም መፋሰስ ምክንያት ይሆንና፣ እናም የጌታን ቀጥተኛ መንገድ የሚያጣምም ሊሆን ይች ላል፣ አዎን እናም የብዙ ሰዎችን ነፍስ ያጠ ፋል።

፰ አሁን እንዲህ እላችኋለሁ ብልሆች እን ሁን፣ እናም እነዚህን ነገሮች እንመርምር፣ ልጄን የማጥፋት ምንም መብት የለንም፣

[ሀ] ሞዛያ ፳፡፲–፲፪።
[ለ] ኤተር ፩፡፩–፭።
[ሐ] ዘፍጥ. ፲፩፡፮–፱።

[ሀ] አልማ ፴፯፡፲–፲።

[ሀ] ቅ.መ.መ. ኡሪም እና ቱሚም።
[ሐ] ቅ.መ.መ. ቅዱሳት መጻህፍት—የሚጠበቁ ቅዱስ መጻፍህት።

፳፯፡፲ [ሀ] ሞዛያ ፳፯፡፴፯።
[ለ] ፩ ሳሙ. ፰፡፱–፲፡፡

ወይም በእርሱ ቦታ ሌላ የሚተካውንም የማ
ጥፋት መብት የለንም።
፴ እናም ልጄ በድጋሚ ወደ ኩራቱና ወደ
ከንቱ ነገሮች የሚመለስ ከሆነ የተናገራቸ
ውን ነገሮች መልሶ ከወሰደ፣ እናም ለመ
ንግስቱ መብቱን ይገባኛል የሚል ከሆነ፣
ይህም እርሱን እናም ደግሞ ህዝቡን ኃጢ
ያት እንዲፈፅሙ ያደርጋልና።
፴፩ እናም አሁን ብልህ እንሁንና፣ እነዚህን
ነገሮች እንመልከት፣ ለዚህም ህዝብ ሰላምን
የሚያረጋግጥለትን ነገር እንስራ።
፴፪ ስለዚህ በተቀሩት ቀናቴ ንጉሳችሁ
እሆናለሁ፤ ይሁን እንጂ፣ በህጋችን መሰ
ረት ለዚህ ህዝብ እንዲፈርዱ [ሀ]ዳኞችን [ለ]እን
ሹም፤ እናም ለዚህ ህዝብ እንደ አዲስ ስልት
እናዘጋጅለት፣ ዳኞች እንዲሆኑ ብልህ ሰዎ
ችን እንሾማለንና፣ እነርሱም በእግዚአብ
ሔር ትዕዛዛት መሰረት ይዳኙአቸዋልና።
፴፫ አሁን ሰው ከሰው ይልቅ በእግዚአ
ብሔር ቢፈረድበት ይሻለዋል፣ የእግዚ
አብሔር ፍርድ ሁልጊዜም ጻድቅ ነውና፣
ነገር ግን የሰው ፍርድ ሁልጊዜ ጻድቅ አይ
ደለም።
፴፫ ስለዚህ፣ የእግዚአብሔርን ህግጋት
የሚመሰርቱ፣ እናም በትዕዛዛቱ መሰረት
በዚህ ህዝብ ላይ የሚፈርዱ [ሀ]ትክክለኛ ሰዎች
የእናንተ ንጉስ እንዲሆኑ ቢቻል፣ አዎን፣
አባቴ [ለ]ቢንያም ለዚህ ህዝብ እንዳደረገው
የሚሰራ ሰው ንጉስ ሊኖራችሁ ቢችል—
እላችኋለሁ፣ ሁልጊዜም ሁኔታው ይህ
መሆን ከቻለ እናንተን የሚገዛ ንጉስ ሁል
ጊዜም ቢኖራችሁ አስፈላጊ ነው።
፴፬ እናም እኔም እንኳን ብሆን በሁሉም
ኃይልና ባለኝ ችሎታ፣ የእግዚአብሔርን
ትዕዛዛት ላስተምራችሁ እናም በምድሪቱ
ላይ ሰላምን ለማስፈን፣ ምንም ዓይነት ጦር
ነትም ሆነ ፀብ፣ ስርቆት፣ ወይም ዝርፊያ፣
ወይም ግድያ፣ ወይም ማንኛውም ዓይነት
ኃጢያት እንዳይኖር ሰርቼአለሁ፣
፴፭ እናም ኃጢያትን የፈፀመውን በፈፀ
መው ወንጀል መሰረት በአባቶቻችን በተ
ሰጠን ህግ መሰረት [ሀ]ቀጥቼዋለሁ።
፴፮ አሁን እላችኋለሁ፣ ሁሉም ሰው ጻድቅ
ባለመሆኑ እናንተን የሚገዙ ንጉሶችም ሆኑ
ንጉስ አስፈላጊ አይደለም።
፴፯ እነሆም፤ አንድ [ሀ]ኃጢአተኛ ንጉስ
ምን ያህል [ለ]ኃጢያት እንዲፈፅም ያደር
ጋል፤ አዎን፣ እናም እንዴት ታላቅ የሆነ
ጥፋት!
፴፰ አዎን፣ የንጉስ ኖህን፣ [ሀ]ኃጢአቱንና
እርኩሰቱን፣ እናም ደግሞ የህዝቡን ኃጢያ
ትና እርኩሰት አስተውሉ። እነሆ ምን ያህል
ታላቅ እርኩሰት በእነርሱ ላይ ሆነ፤ እናም
ደግሞ በኃጢአታቸው የተነሳ ወደ [ለ]ባርነት
ተወሰዱ።
፴፱ እናም በጥበበኛው ፈጣሪአቸው ጣልቃ
ገብነት፣ እና ይህም በጥልቁ ንስሃቸው ምክ
ንያት፣ ባይሆን ኖሮ እስካሁን ድረስ በማ
ይታመን ሁኔታ በባርነት ሊቀሩ ይገባቸው
ነበር።
፵ ነገር ግን እነሆ በእርሱ ፊት እራሳቸ
ውን [ሀ]ትሁት በማድረጋቸው እነርሱን አዳ
ናቸው፤ እናም [ለ]በኃይል ወደእርሱ በመ
ጮሀቸው ከባርነት አዳናቸው፣ እናም ጌታ
በእርሱ ላይ [ሐ]እምነታቸውን በጣሉት [መ]የም
ህረት ክንዱን በመዘርጋት በሁሉም ሁኔታ
ዎች ከሰዎች ልጆች መካከል በኃይሉ እን
ደዚህ ይሠራል።
፵፩ እናም እነሆ፣ አሁን እላችኋለሁ በብዙ
ፀብና ደም መፋሰስ ካልሆነ በቀር ክፉውን
ንጉስ ልታስወግዱት አይቻላችሁም።
፵፪ እነሆ በክፋት ያሉ [ሀ]ወዳጆች ስለአ
ሉት፣ እናም ጠባቂዎቹን በእርሱ ዙሪያ ያስ
ቀምጣቸዋል፤ እናም ከእርሱ በፊት በፅድቅ

፲፩ [ሀ] ዘፀአ. ፲፰፡፲፫–፳፡፡
[ለ] ሞዛያ ፳፱፡፳፩–፳፯፡፡
፲፫ [ሀ] ሞዛያ ፳፫፡፳፣ ፲፫–፲፡፡
[ለ] ቃላት ፩፡፲፯–፲፰፡፡
፲፭ [ሀ] አልማ ፩፡ ፴፱–፴፫፡፡
፲፯ [ሀ] ሞዛያ ፳፫፡፲–፱፡፡
[ለ] አልማ ፵፯፡ ፱–፲፡፡
፲፰ [ሀ] ሞዛያ ፲፩፡ ፩–፲፭፡፡
[ለ] ፩ ሳሙ. ፰፡ ፲–፲፰፣
ሞዛያ ፲፪፡ ፩–፰፣
ኤተር ፮፡ ፳፪–፳፫፡፡
፳ [ሀ] ሞዛያ ፳፩፡ ፲፫–፲፭፡፡
[ለ] ዘፀአ. ፪፡ ፳፫–፳፭፣
አልማ ፵፫፡ ፵፱–፶፡፡
[ሐ] ቅ.መ.መ. መታመን፡፡
[መ] ሕዝ. ፴፫፡ ፲፩፣ ፲፭–፲፯፣
ሞዛያ ፳፣ ፲፡ ፴፡፡
፳፪ [ሀ] ፩ ነገሥ. ፲፪፡ ፰–፲፩፡፡

የነገሱትን ሰዎች ህግ ያጠፋል፣ የእግዚአብ ሔርን ትዕዛዛት በእግሩ ይረጋግጠዋልም።

፳፫ እናም ህጎችን ያወጣል፣ በህዝቡ መካ ከልም ይልካል፣ አዎን እንደ እርሱ ᵐክፋት የሆኑ ህጎችን፤ እናም ህጉን ያልተቀበለ እን ዲጠፋ ይደረጋል፤ በእነርሱም ላይ የሚ ያምፅ ለጦርነት ወታደሮቹን በእነርሱ ላይ ይልካል፤ እናም የሚችል ከሆነ ያጠፋቸ ዋል፤ ፃድቅ ያልሆነ ንጉስም የፃድቃንን መንገድ በሙሉ እንደዚህ ያጣምማል።

፳፬ እናም አሁን እነሆ እላችኋለሁ እንደ ዚህ አይነት እርኩሰት በእናንተ ላይ መም ጣቱ አስፈላጊ አይደለም።

፳፭ ስለዚህ ትክክለኛ የሆነው እናም በጌታ እጅ የተሰጠው በአባቶቻችን በተሰጣችሁ ህጎች መሰረት ይፈረድባችሁ ዘንድ በዚህ ህዝብ ድጋፍ ዳኛን ምረጡ።

፳፮ አሁን ህዝቡ ትክክለኛ ከሆነው ከማ ንኛውም ነገር ተቃራኒ የሆነ ድምፅ መፈ ለግ የተለመደ አይደለም፤ ነገር ግን ትክ ክል ያልሆነውን መፈለግ በትንሹ የህብረተ ሰብ ክፍል የተለመደ ነው፤ ስለዚህ ይህ ንን ጠብቁ እናም የራሳችሁ ህግ አድር ጉት—በህዝቡም ድምፅ ጉዳያችሁን እን ድትፈፅሙ።

፳፯ እናም የህዝቡ ድምፅ መጥፎውን የሚ መርጥበት ᵐጊዜ ከመጣ፣ የእግዚአብሔር ፍርድ በእናንተ ላይ የሚመጣበት ጊዜ ይሆ ናል፤ አዎን ከዚህ በፊት ይህንን ምድር እን ደጎበኘው እናንተን በታላቅ ጥፋት የሚጎበ ኝበት ጊዜ ይሆናል።

፳፰ እናም አሁን መሳፍንቶች ካሏችሁና በተሰጣችሁ ህግ መሰረት የሚፈርዱባችሁ ካልሆነ በጠቅላይ ዳኛ እንዲፈረድባቸው ማድረግ ትችላላችሁ።

፳፱ ጠቅላይ ዳኞቻችሁ ጽድቅ ፍርድ ካልፈረዱላችሁ፣ አነስተኞች የበታች ዳኛ ዎቻችሁ በአንድነት እንዲሰበሰቡ ታደርጋ ላችሁ፣ እና እነርሱም በጠቅላይ ዳኞቻችሁ ላይ በህዝቡ ድምፅ መሰረት ይፈርዳሉ።

፴ እናም በጌታ ፍራቻ እነዚህን ነገሮች እን ድታደርጉ አዛችኋለሁ፤ እናም ንጉስ እንዳ ይኖራችሁ እነዚህን ነገሮች እንድታደርጉ አዛችኋለሁ፤ ይህ ህዝብ ኃጢያትና ክፋትን ከፈፀመ በራሳቸው ላይ መልስን ያገኛሉ።

፴፩ እነሆም እላችኋለሁ፣ የብዙዎች ኃጢያት የሆነው በንጉሶቻቸው ክፋት ምክ ንያት ነው፤ ስለዚህ ክፋታቸው በንጉሶቻ ቸው ራስ ላይ ይመለሳሉ።

፴፪ እናም አሁን በዚህ ምድር ᵐአድልዎ ከእንግዲህ በዚህ ምድር፣ በተለይ በህዝቤ መካከል እንዲኖር አልፈልግም፤ ነገር ግን ይህ ምድር ᵃየነፃነት ምድር እንዲሆን እፈ ልጋለሁ፣ እናም ጌታ ምድሪቱን እንድን ኖርበትና እንድንወርስ አስፈላጊ ነው እስ ካለ ድረስ፣ አዎን፣ ᵃማንኛውም ሰው የእኛ ዘር በምድር ፊት እስከቀረበም ድረስ ማን ኛውም ሰው በእኩል ልዩ መብቱንና እድ ሎቹን ይደሰትባቸው።

፴፫ እናም ንጉስ ሞዛያ፣ የፃድቃኑን ንጉስ ፍርድና ችግር ሁሉ በማያያዝ፣ አዎን፣ ለህ ዝባቸው ያላቸው የመንፈስ ስቃይ ሁሉ፣ እናም ደግሞ በንጉሱ ላይ የህዝቡን ማጉረ ምረምን በመግለፅ ከዚህ የበለጡ ብዙ ነገ ሮችን ፅፎላቸዋል፤ እናም ይህንን ሁሉ ገል ፆላቸዋል።

፴፬ እናም እነዚህ ነገሮች መሆን እንደ ሌለባቸው ነግሯቸዋል፣ ነገር ግን ሸክሙ በህዝቡ ላይ ሁሉ ላይ መምጣት አለበት፣ እያንዳንዱም ሰው የእራሱን ክፍል ይሸ ከም ዘንድ።

፴፭ እናም ደግሞ ፃድቅ ባልሆነ ንጉስ በመገዛታቸው፣ ጥቅም በሌለው የደከሙ በትን እንዲያውቁ አደረገ።

፴፮ አዎን፣ ሁሉም ክፋቶቹንና እርኩ ሶቹን፣ እናም ጦርነቶችን፣ ፀቦችንም፣ ደም መፋሰስንም፣ ስርቆትንም፣ ዝርፊያ ንም፣ ዝሙትንም መፈፀም፣ እናም ሊቆ ጠሩ የማይችሉ ሁሉም አይነት ክፋት—እነዚህ ነገሮች መሆን እንደሌለባቸው ከእ

ᵃ፳፫ ᴴ ቅ.መ.መ. ክፉ፣ ክፋት።
ᵃ፳፮ ᴴ አልማ ፲፡፲፱።
ᵃ፴ ᴴ አልማ ፴፡፲፩።
ᵃ ፪ ኔፊ ፩፡፯፣ ፲፡፲፩።
ᵃᵐ ቅ.መ.መ. መብት።
ᵃᵃ አልማ ፳፯፡፱።

ግዚአብሔርም ትዕዛዛት ጋር ተፃራሪ መሆ ናቸውን ተናገረ።

፴፯ እናም አሁን እንዲህ ሆነ፣ ንጉስ ሞዛያ እነዚህን ነገሮች በህዝቡ መካከል ከላከ በኋላ የእርሱ ቃላት እውነት እንደሆኑ ታመኑ።

፴፰ ስለዚህ ለንጉስ ያላቸውን ፍላጎት ተዉ፣ እናም በምድሪቱ ሁሉም ሰው እኩል እድል እንዲኖረው እጅግ ጓጉ፤ አዎን፣ እናም እያንዳንዱ ሰው የራሱን ኃጢያት ለመመለስ ፈቃደኝነቱን ገለፀ።

፴፱ ስለዚህ እንዲህ ሆነ በምድሪቱ ላይ ሁሉ በተሰጠው ᵐህግ መሰረት እነርሱን የሚፈርድ ዳኛ ማን መሆን እንዳለበት በሚ መለከት ድምጻቸውን ለመስጠት በቡድን እራሳቸውን በአንድነት ሰበሰቡ፣ እናም በተሰጣቸው ᵃነፃነት የተነሳ እጅግ ተደስ ተው ነበር።

፴ እናም በሞዛያ ያላቸው ፍቅር ጠነከረ፤ አዎን፣ ከማንም ሰው የበለጠ አከበሩት፤ ጥቅም፣ አዎን ነፍስን የሚያስረክሰውን አስ ቀያሚ ገንዘብ፣ የሚፈልግ ጨካኝ እንደ ሆነ አድርገው አልተመለከቱትም፤ ከእነር ሱም ሀብታቸውን ለመውሰድ አልፈለገም፣ ወይም በደም መፋሰስም አልተደሰተምና፤ ነገር ግን በምድሪቱ ᵐሰላምን መስርቷል፣ እናም ለህዝቡ ከሁሉም ባርነት እንዲለቀቁ አድርጓል፤ ስለዚህም፣ አዎን፣ እጅግ ከልክ በላይ አከበሩት።

፴፩ እናም እንዲህ ሆነ በእነርሱ ላይ የሚ ገዙ ᵐዳኛዎችን፣ ወይንም በህጉ መሰረት የሚዳኛቸውን ᵐሙ፤ እናም ይህንን በም ድሪቱ ዙሪያ ሁሉ አደረጉ።

፴፪ እናም እንዲህ ሆነ አልማ የመጀመሪያ ዋና ዳኛ በመሆን ተመረጠ፣ አባቱም ሀላፊ ነቱን ለእርሱ በመስጠቱ፣ እናም የቤተክር ስቲያኑን ጉዳዮች ሁሉ በሚመለከት ሀላፊ ነቱን ስለሰጠው ደግሞ ሊቀ ካህንም ነበር።

፴፫ እናም አሁን እንዲህ ሆነ አልማ ᵐበጌታ መንገድ ተራመደና፣ ትዕዛዛቱን ጠበቀ፣ እናም ጻድቅ ፍርድን ፈረደ፤ እናም በም ድሪቱ ሁሉ የማያቋርጥ ሰላም ነበረ።

፴፬ እናም ኔፋውያን ከሚባሉ ህዝቦች መካከል ሁሉ በዛራሔምላ ምድር የዳኛ ዎች አገዛዝ እንደዚህ ተጀመረ፣ እናም አልማ የመጀመሪያውና ዋናው ዳኛ ነበር።

፴፭ እናም አሁን እንዲህ ሆነ ሰማንያ ሁለት ዓመት ሆኖት አባቱ ሞተ፤ እርሱም የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት በመፈፀም ይኖር ነበር።

፴፮ እናም እንዲህ ሆነ በንግስናው ሠላሳ ሶስተኛ ዓመት፣ ᵐስልሳ ሦስት ዓመት ሆኖት ሞዛያም ደግሞ ሞተ፤ ይህም በአጠቃላይ ሌሂ ኢየሩሳሌምን ለቆ ከወጣ አምስት መቶ ዘጠኝ ዓመት ነበር።

፴፯ እናም በኔፊ ህዝብ ላይ የነገስት አገዛዝ በዚሁ አበቃ፣ እናም የቤተክርስቲያናቸው መስራች የነበረው የአልማ ቀናትም እንደ ዚህ ተፈፀሙ።

መፅሐፈ አልማ

የአልማ ልጅ

የአልማ ልጅ፣ በኔፊ ህዝብ ላይ የመጀመሪያውና ዋናው ዳኛ፣ እናም ደግሞ የቤተክርስቲ ያኗ ሊቀ ካህን የሆነው፣ የአልማ ታሪክ። የመሣፍንት የንግስ፣ እናም በህዝቡ መካከል የነ በረው የጦርነትና ፀብ ታሪክ። እናም ደግሞ የመጀመሪያውና ዋናው ዳኛ በሆነው በአልማ መዝገብ መሰረት በኔፋውያንና በላማናውያን መካከል የነበረው የጦርነት ታሪክ።

፴፱ ᵃ አልማ ፩፡ ፲፱።
ᵇ ቅ.መ.መ. መብት።
፴ ᶜ ቅ.መ.መ. ሰላም የሚሰራ።
፴፩ ᵃ ሞዛያ ፳፱፡ ፲፩።
፴፫ ᵃ ቅ.መ.መ. መራመድ፣ ከእግዚአብሔር ጋር
መራመድ (መሄድ)።
፴፮ ᵃ ሞዛያ ፮፡ ፱።

ምዕራፍ ፩

ኔሆር ሀሰተኛ ትምህርት አስተማረ፣ ቤተ ክርስቲያንን አቋቋመ፣ የካህን ተንኮልን ጀመረ፣ እናም ጌዴዎንን ገደለው—ኔሆር የተሰቀለው በወንጀሉ ነው—የካህን ተንኮ ልና ስደት በህዝቡ መካከል ተሰፋፋ—ካህ ናት ራሳቸውን በራሳቸው ይረዳሉ፣ ህዝቡ ለድሆች እንክብካቤ አደረጉ፣ እናም ቤተ ክርስቲያኗ በለፀገች። ከ፣፲፩–፲፰ ም.ዓ. ገደማ።

እናም እንዲህ ሆነ መሳፍንቶች በኔፊ ህዝብ ላይ በነገሱበት በመጀመሪያው ዓመት፣ ንጉስ ሞዛያ በቦታውም ማንም እን ዲነግስ ሳያደርግ፣ [ሀ]ምድር ሁሉ ወደሚሄ ዱበት ሄዷል፣ መልካሙን ገድል ተጋድ ሏል፣ በእግዚአብሔር ፊት በልበ ቅንነት ተራምዷል፤ ይሁን እንጂ [ለ]ህግጋትን አቋ ቁሟል፣ እናም እነርሱም በህዝቡ ዘንድ ተቀባይነትን አግኝተዋል፣ ስለሆነም፣ ከዚ ህም ጊዜ በኋላ፣ ህዝቡ እርሱ ባቋቋመው ህግጋት ለመገዛት ተገደው ነበር።

፪ እናም እንዲህ ሆነ በአልማ በዳኝነት መቀመጫ ላይ በሚነግስበት በመጀመሪያው ዓመት፣ አንድ [ሐ]ሰው እንዲፈረድበት ወደ ፍርድ ወንበሩ አምጥተውት ነበር፤ ሰውየ ውም ትልቅ የነበረ እና በጥንካሬውም የሚ ታወቅ ነበር።

፫ እናም ይህ ሰው ከህዝቡ መካከል በመ ሄድ እርሱ [መ]የእግዚአብሔር ቃል ብሎ ያለ ውን በመስበክ፣ [ሠ]የቤተክርስቲያኗ ተቃራኒ በመሆን፣ ለህዝቡም ካህንና መምህር ሁሉ [ረ]ታዋቂ መሆን እንዳለባቸው፣ እናም በእ ጃቸውም [ሰ]መስራት እንደሌለባቸው፣ ነገር ግን በህዝቡ መደገፍ እንዳለባቸው ያውጅ ነበር።

፬ እናም ደግሞ ለህዝቡ የሰው ዘር ሁሉ በመጨረሻው ቀን መዳን እንዳለበት፣ እናም መፍራትም ሆነ መንቀጥቀጥ እንደ ሌለባቸው፣ ነገር ግን ጌታ ሁሉን በመፍጠ ሩና ደግሞም ሁሉን በማዳኑ እራሳቸውን በማቅናት እንዲደሰቱ፣ እንዲሁም በመጨ ረሻ ሁሉም ሰው ዘለአለማዊ ህይወት ሊኖ ረው ይገባል በማለት መሰከረ።

፭ እናም እንዲህ ሆነ እነዚህን ነገሮች በብዛት አስተምሮ ብዙዎች የእርሱን ቃላት አመኑ፣ ይህም ሆኖ ብዙዎች እን ኳን እርሱን መደገፍ እናም ገንዘብ ይሰ ጡት ጀመር።

፮ እናም በልቡ ኩራት መወጠር፣ እናም ውድ ልብስ መልበስ ጀመረ፤ አዎን፣ እናም ከሰበካው ጋር በሚዛመድ ሁኔታ እንኳን [ሀ]ቤተክርስቲያንን ማቋቋም ጀመረ።

፯ እናም እንዲህ ሆነ በቃሉ ላመኑት ለመ ስበክ በመጓዝ ላይ እንዳለ በእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን አባል፣ አዎን፣ የእነርሱም መምህር የነበረ፣ አንድን ሰው አገኘ፤ እናም የቤተክርስቲያኗን ሰዎችም ይለውጣቸው ዘንድ፣ ከእርሱ ጋር በኃይል መከራከር ጀመረ፤ ነገር ግን [ሀ]በእግዚአብሔር ቃል በመገሰፅ ሰውየው ተቃወመው።

፰ የሰውየው ስምም [ለ]ጌዴዎን ነበር፤ እናም የሊምሂን ህዝብ ከባርነት ለማስለ ቀቅ በእግዚአብሔር እጅ መሳሪያ የነበረው እርሱ ነበር።

፱ አሁን ጌዴዎን በእግዚአብሔር ቃል ስለተቃወመው በጊድዮን ተቆጣ፤ እናም ጎራዴውን መዘዘና ይመታው ጀመረ። እንግዲህ ጌዴዎን በማርጀቱ ምቱን ለመ ቋቋም አልቻለም ነበር፣ ስለሆነም በጎራ ዴው [ሐ]ሞተ።

፲ እናም ገዳዩ በቤተክርስቲያኗ ሰዎች ተወሰደ፣ እናም በፈፀመው ወንጀል [መ]እን ዲፈረድበት በአልማ ፊት ቀረበ።

፩ ፩ *ሀ* ሞዛያ ፳፱፡ ፴፮።
ለ ጂረም ፩፡ ፭፤ አልማ ፬፡ ፲፯፤ ሔለ. ፪፡ ፳፪።
፪ *ሀ* አልማ ፩፡ ፲፭።
፫ *ሀ* ሕዝ. ፲፫፡ ፫።
ለ ቅ.መ.መ. የክርስቶስ ተቃዋሚ።
ሐ ሉቃ. ፮፡ ፳፮፤ ፩ ኔፊ ፳፪፡ ፳፫።
መ ሞዛያ ፲፰፡ ፳፬፣ ፳፮፤ ፳፯፡ ፭።
፮ *ሀ* ፩ ኔፊ ፲፬፡ ፲።
፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ቃል።
፰ *ሀ* ሞዛያ ፳፡ ፲፯፤ ፳፪፡ ፫።
፱ *ሀ* አልማ ፮፡ ፯።
፲ *ሀ* ሞዛያ ፳፱፡ ፴፪።

፲፩ እናም እንዲህ ሆነ ከአልማ ፊት ቆመና በታላቅ ድፍረት ለራሱ ተከራከረ።

፲፪ ነገር ግን አልማ እንዲህ ሲል ተናገረው፡ እነሆ በዚህ ህዝብ መካከል የካህን ተንኮል ከተጀመረበት ጊዜ ይህ የመጀመሪያው ነው። እናም እነሆ አንተ ᵐበካህን ተንኮል ብቻ አይደለም ጥፋተኛ የሆን ከው፣ ነገር ግን ይህን በጎራዴው ለማስገደድ ጥረት አድርገሀል፤ እናም የካህን ተንኮል በህዝቡ መካከል በግዴታ የሚደረግ ቢሆን ይህም አጠቃላይ ጥፋታቸውን ያስከትላል።

፲፫ እናም አንተ የፃድቁን ደም አፍስ ሰሀል፣ አዎን፣ በዚህ ህዝብ መካከል ብዙ መልካምን ያደረገውን ሰው፤ እናም አን ተን እንድትተርፍ ካደረግን የእርሱ ደም ᵐለበቀል በእኛ ላይ ይመጣል።

፲፬ ስለሆነም የመጨረሻው ንጉሳችን በሆ ነው በሞዛያ በተሰጠን ህግ መሰረት እንድ ትሞት ᵐተፈርዶብሀል፤ እናም ህጉ በህ ዝቡ ተቀባይነት አግኝቶአል፤ ስለዚህ ህዝቡ በህጉ መተዳደር አለበት።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ እርሱንም ወሰ ዱት፤ ስሙም ᵐኔሆር ነበር፤ እናም ወደ ማንቲ ኮረብታ ጫፍ ወሰዱት፤ እናም በእ ዚያ ለህዝቡም ያስተማረው ከእግዚአብ ሔር ቃል ጋር ተቃራኒ እንደነበረ በሰማ ይና በምድር መካከል ተቀባይ እንዲሆን ተገደደ ወይም ተቀበለ፤ እናም በእዚያም በአሳፋሪ ᵃሞት ተሰቃየ።

፲፮ ይሁን እንጂ፣ ይህ የካህን ተንኮል በም ድሪቱ እንዳይስፋፋ ገደብ አልሆነም፣ ምክ ንያቱም የዓለምን ከንቱ ነገሮች የሚያፈቅሩ ብዙዎች ነበሩና፣ እናም ሐሰተኛ ትምህር ቶችን በመስበክ ሄዱ፤ እናም ይህንን ያደረ ጉት ᵐለሀብትና ለክብራቸው ነበር።

፲፯ ይሁን እንጂ፣ ህጉን በመፍራት ᵐለመ ዋሸት አይደፍሩም ነበር፣ ምክንያቱም ይህ ቢታወቅ ኖሮ ሀሰተኞች ይቀጣሉና፤ ስለሆ ነም በእምነታቸው እንደሚሰብኩ ያስመስ ላሉ፤ እናም አሁን ህጉ በማንኛውም ሰው ᵃእምነት ላይ ስልጣን ሊኖረው አይችልም።

፲፰ እናም ህጉን በመፍራት ᵐለመስረቅ አልደፈሩም፤ እንደነዚህ አይነቶች ተቀ ጥተዋልና፤ ለመዝረፍም ሆነ፣ ᵃለመግደል አልደፈሩም፣ የገደለ ᶜበሞት ይቀጣልና።

፲፱ ነገር ግን እንዲህ ሆነ የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን አባል ያልሆኑት የእግዚአብ ሔር ቤተክርስቲያን አባል የሆኑትን፣ እናም በራሳቸው ላይ የክርስቶስን ስም የለበሱትን አሳደዱ።

፳ አዎን እነርሱንም አባረሩአቸው፣ እናም በሁሉም ዓይነት ቃላት አሰቃዩአ ቸው፣ ይህም በትህትናቸው የተነሳ፣ እናም በአመለካከታቸው ኩሩ ስላልነበሩና፣ የእ ግዚአብሔርን ቃል ᵐያለገንዘብና ያለምንም ክፍያ እንዳቸው ለሌላኛው የሚካፈሉ ስለ ነበሩ ነው።

፳፩ እንግዲህ በቤተክርስቲያኗ አባል የሆነ ማንም ሰው በቤተክርስቲያኗ አባል ያልሆኑ ትን ተነስቶ የሚያሳድድ መኖር እንደሌለ በት፣ እናም በመካከላቸውም ምንም ᵐስደት መኖር እንደሌለበት በቤተክርስቲያኗ ሰዎች መካከል ህጉ ጥብቅ ነበር።

፳፪ ይሁን እንጂ፣ ከእነርሱ መካከል ብዙ መኩራት የጀመሩ፣ እናም ከጠላቶቻቸው ጋር፣ እስከመመታታትም ድረስ፣ በኃይል መጣላት የጀመሩ ነብሩ፣ አዎን፣ በቡጢም አንዱ በሌላኛው ይመታታሉ።

፳፫ አሁን ይህ በአልማ ሁለተኛው የንግስ ዓመት ውስጥ ነበር፤ እናም ለቤተክርስቲ ያኗ ታላቅ ስቃይ ምክንያት ነበር፤ አዎን፣ ለቤተክርስቲያኗ ታላቅ ፈተና ምክንያት ነበር።

፳፬ የብዙዎች ልብ ጠጥሯል፣ እናም ከእ

፲፪ ᵃ ፪ ኔፊ ፳፯፡፳፱። ᵇ ቅ.መ.መ. የካህን ተንኮል።
፲፫ ᵃ ቅ.መ.መ. በቀል።
፲፬ ᵃ ቅ.መ.መ. የሞት ቅጣት።
፲፭ ᵃ አልማ ፩፡ ፪። ᵇ ዘዳግ. ፲፫፡ ፩–፱።
፲፮ ᵃ ቅ.መ.መ. ሀብቶች፤ ከንቱ፣ ከንቱነት።
፲፯ ᵃ ቅ.መ.መ. ሐሰት፤ ታማኝ፣ ታማኝነት። ᵇ አልማ ፴፡ ፯–፲፪፤ ኢ.ኦ. ፩፡ ፲፩።
፲፰ ᵃ ቅ.መ.መ. መስረቅ። ᵇ ቅ.መ.መ. ግድያ። ᶜ ቅ.መ.መ. የሞት ቅጣት።
፳ ᵃ ኢሳ. ፶፭፡ ፩–፪።
፳፩ ᵃ ቅ.መ.መ. ማሳደድ፣ መሳደድ።

ንግዲህ በእግዚአብሔር ሰዎች መካከል እን ዳይታወሱም ስማቸው ᵐተደምሠዋልና። እናም ደግሞ ብዙዎች ራሳቸውን ከመካ ከላቸው ᵃአወጡ።

፳፭ አሁን በእምነታቸው ፀንተው ለቆሙ ይህ ታላቅ ችግር ነበር፤ ይሁን እንጂ፣ የእ ግዚአብሔርን ትዕዛዛት በመጠበቅ ፅኑና የማይነቃነቁ ነበሩ፣ እናም በላያቸው ላይ የተቆለለውን ጭቆና ᵐበትዕግስት ተወጡ።

፳፮ እናም ካህናት የእግዚአብሔርን ቃል ለህዝቡ ለመናገር ᵐስራቸውን በተዉ ጊዜ፣ ሰዎቹም ቢሆኑ የእግዚአብሔርን ቃል ለማ ዳመጥ ስራቸውን ትተዋል። እናም ካህናት የእግዚአብሔርን ቃል በተናገሩ ጊዜ በድ ጋሚ ወደ ስራዎቻቸው በትጋት ተመለሱ፤ እናም ካህኑም፣ እራሱን ከአድማጩ በላይ አላደረገም፣ ምክንያቱም ሰባኪው ከአ ድማጩ የተሻለ፣ መምህሩም ከተማሪው ምንም የተሻለ አልነበረም፤ እናም ሁሉም እኩል ነበሩና፣ ሁሉም ሰዎች ᵃበጥንካሬአ ቸው መሰረት ስራቸውን ይሰራሉ።

፳፯ እናም ማንኛውም ሰው ᵐለድሆችና ለችግረኞች፣ እናም ለታመሙና፣ ለተሰቃ ዩት ባላቸው መጠን ᵃከቁሳቁሶቻቸው አካ ፈሉ፤ እናም እነርሱ ውድ ልብሶችን አል ለበሱም ነበር፣ ይሁን እንጂ ንፁህና የደ ስደስ ያላቸው ነበሩ።

፳፰ እና እንደዚህም የቤተክርስቲያን ጉዳ ዮችን አቋቋሙ፤ እና እንደዚህም ይህ ሁሉ ጭቆና ቢኖርባቸውም የማያቋርጥ ሰላም በድጋሚ ይኖራቸው ጀመር።

፳፱ እናም አሁን፣ በቤተክርስቲያኗ ፅኑ ነት የተነሳ እጅግ ᵐሀብታም መሆን ጀመሩ፣ ሁሉም የሚያስፈልጋቸው ማንኛውም ነገ ሮች በብዛት ነበራቸው—ብዙ መንጋዎችና ከብቶች፣ ሁሉም ዓይነት ኮርማዎችም፣ ደግሞም ብዙ ጥራጥሬና፣ ወርቅ፣ ብርና፣ የከበሩ ነገሮች፣ እናም ብዙ ᵃሐርና የተ ፈተለ ጥሩ በፍታ፣ እናም ሁሉም ዓይነት መልካም ልብሶች ነበሯቸው።

፴ እናም እንዲሁ፣ ᵐበብልፅግናቸው ᵃየተ ራቁትን ወይም የተራቡትን፣ ወይም የተ ጠሙት፣ የታመሙትን ወይም ያልተመ ገቡትን ቢሆን ማንንም አላባረሩም፤ እናም ልባቸውን በሀብት ላይ አላደረጉም፤ ስለ ዚህ ለሁሉም፣ ለወጣቶችም ሆነ ለሽማግ ሌዎች፣ ለታሰሩትም ሆነ ነፃ ለሆኑት፣ ለወ ንድም ሆነ ለሴት፣ ከቤተክርስቲያን ለሆ ኑም ሆነ ላልሆኑት ደግ ነበሩ፤ በችግር ለነ በሩት እንዳደረጉት ሁሉ በሰዎች ፊት ᵃአላ ደሉም።

፴፩ እናም በለፀጉና ከእነርሱ ቤተክርስቲ ያን ካልሆኑት በበለጠ ሀብታም ሆኑ።

፴፪ ከእነርሱ ቤተክርስቲያን ያልሆኑት ራሳቸውን በጥንቆላና ᵐበጣኦት አምላኪነት ወይም ᵃበስንፍና እናም ᵃᵃበከንቱ ልፍለፋ እናም ᵐበቅናትና ክርክር፣ ውድ ልብሶ ችን በመልበስ፣ በትዕቢት በራሳቸው አይን ᵐበመነፋት፣ በማሳደድ፣ በመዋሸት፣ በመ ስረቅ፣ በመዝረፍ፣ ዝሙትን በመፈፀምና፣ በመግደል፣ እናም ሁሉንም ዓይነት ኃጢ ያት በመፈፀም ራሳቸውን አስደሰቱ፤ ይሁን እንጂ፣ ህጉ በሚቻለው መጠን በተላለፉት ሁሉ ላይ በኃይል ተደርጓል።

፴፫ እናም እንዲህ ሆነ እንደዚህ ህግን በእ ነርሱ ላይ በማሳረፍ፣ እያንዳንዱ ሰው በሰ

፳፩ *ሀ* ዘፀአ. ፴፪፡፴፣ ፴፫፤
ሞዛያ ፳፯፡፴፣ ፴፯፤
አልማ ፮፡፫፡ ፫።
ቅ.መ.መ. ውግዘት።
ለ አልማ ፵፯፡ ፯።
ቅ.መ.መ. ክህደት።
፳፭ *ሀ* ቅ.መ.መ. ትዕግስት።
፳፯ *ሀ* ሞዛያ ፲፰፡፳፡ ፳፯፤
፳፯፡ ፫–፭።
ለ ሞዛያ ፬፡ ፳፯፣
ት.እና ቃ. ፲፡ ፬።
፳፯ *ሀ* ሉቃ. ፲፰፡ ፳፪፤
ሞዛያ ፬፡ ፳፯፣
ት.እና ቃ. ፵፪፡ ፳፬–፴፭።
ለ ቅ.መ.መ. ምዕዋት፣ የምዕዋት ስጦታ።
፳፱ *ሀ* ቅ.መ.መ. ሀብቶች።
ለ አልማ ፬፡ ፮።
፴ *ሀ* ያዕቆ. ፪፡ ፲፯–፲፱።
ለ ቅ.መ.መ. ደሀ።
ሐ አልማ ፲፯፡ ፲፰፤
ት.እና ቃ. ፭፡ ፴፭።
፴፪ *ሀ* ቅ.መ.መ. ጣኦት አምላኪ።
ለ ቅ.መ.መ. ስራ ሰልቺ፣ ስራ ፈቺ።
ሐ ቅ.መ.መ. ክፉ መናገር።
መ ቅ.መ.መ. ቅናት።
ሠ ያዕቆ. ፪፡ ፲፫፤
አልማ ፴፭፡ ፳፭፣
ሞር. ፰፡ ፳፰።
ቅ.መ.መ. ኩራት።

ራው መሰረት እየተቀጣ፣ እነርሱም ይበልጥ ተረጋጉ፣ እናም የሚታወቅ ከሆነ ምንም ዓይነት ኃጢያት ለመፈፀም አልደፈሩም፤ ስለዚህ፣ እስከ አምስተኛው ዓመት የመሳፍንት አገዛዝ ድረስ በኔፊ ህዝቦች መካከል ከፍተኛ ሰላም ነበር።

ምዕራፍ ፪

አምሊኪ ንጉስ ለመሆን ፈለገ እናም በህዝቡ ድምፅ ተቀባይነት አላገኘም—ተከታዮቹ ንጉስ አደረጉት—አምሊኪውያን ከኔፋውያን ጋር ተዋጉ እናም ተሸነፉ—ላማናውያንና አምሊኪውያን ኃይላቸውን በአንድ ላይ አደረጉ፣ እናም ተሸነፉ—አልማ አምሊኪን ገደለው። ከ፹፯ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ በአምስተኛው የንግስና ዓመታቸው መጀመሪያ በህዝቡ መካከል ጠብ ተጀመረ፤ እጅግ አጭበርባሪ፣ አዎን ለዓለም ጥበብ ብልህ ሰው የሆነ፣ በህግ መሰረት በተገደለው [ሀ]ጌዴዎንን በገደለው ሰው ሥርዓት መሠረት የነበረው አምሊኪ ተብሎ የሚጠራው ሰው ነበር።

፪ አሁን አምሊኪ በብልህነቱ ብዙ ሰዎች እንዲከተሉት አደረገ፣ ብዙዎች እንኳን ሆነው እጅግ ኃያል መሆን ጀመሩ፤ እናም አምሊኪ በህዝቡ ላይ ንጉስ እንዲሆን ጥረት ማድረግ ጀመሩ።

፫ እንግዲህ ይህ ለቤተክርስቲያኗ ሰዎች፣ እናም ደግሞ በአምሊኪ ጉትጎታ ላልተወሰዱት ሁሉ አስጊ ነበር፤ በህጋቸው መሰረት እንደዚህ ያሉ ነገሮች [ሀ]በህዝቡ ድምፅ መመስረት ያለባቸው እንደሚሆኑ ያውቃሉና።

፬ ስለዚህ አምሊኪ የህዝቡን ድምፅ ማግኘት የሚችል ከሆነ፣ እርሱ ክፉ ሰው ስለነበረ፣ በቤተክርስቲያን ያላቸውን መብትና እድል [ሀ]ይከለክላቸዋል፤ ዓላማው የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን ለማጥፋት ነበርና።

፭ እናም እንዲህ ሆነ እያንዳንዱ ሰው እንደአስተሳሰቡ፣ በአምሊኪ ይሁን ወይም እርሱን ለመቃወም፣ በተለያየ አካል በመሆን፣ አንዱ ከሌላው ጋር ታላቅ ፀብና አስገራሚ [ሀ]ጥል በማድረግ በምድሪቱ ላይ ሁሉ ተሰበሰቡ።

፮ እናም ጉዳዩን በተመለከተ ድምፅ ለመስጠት እራሳቸውን በአንድ ላይ ሰበሰቡ፣ እናም በዳኛዎች ፊት ቀርበው ነበር።

፯ እናም እንዲህ ሆነ የህዝቡ ድምፅ በአምሊኪ ላይ ሆነ፣ እርሱም በህዝቡ ላይ ንጉስ አልተደረገም ነበር።

፰ እንግዲህ ይህ ከእርሱ ተቃራኒ ለሆኑት ታላቅ ደስታን በልባቸው እንዲሆን ያደርጋል፤ ነገር ግን አምሊኪ የእርሱ ደጋፊዎች የሆኑት ደጋፊዎች ያልሆኑት ላይ እንዲያውኩ አደረገ።

፱ እናም እንዲህ ሆነ እራሳቸውን በአንድነት ሰበሰቡ፣ እናም አምሊኪን ንጉስ አድርገው ቀቡት።

፲ እናም አምሊኪ በእነርሱ ላይ ንጉስ በተደረገ ጊዜ እነርሱ በወንድሞቻቸው ላይ የጦር መሳሪያዎቻቸውን እንዲያነሱ አዘዘ፤ እናም ይህንን ያደረገው በእርሱ ስር ያደርጋቸው ዘንድ ነው።

፲፩ እንግዲህ የአምሊኪ ሰዎች [ሀ]አምሊኪውያን ተብለው በአምሊኪ ስም በመጠራት ይታወቃሉ፤ እናም ቀሪዎቹ [ለ]ኔፋውያን፣ ወይም የእግዚአብሔር ሰዎች ተብለው ይጠራሉ።

፲፪ ስለዚህ የኔፋውያን ህዝብ የአምሊኪውያንን ዓላማ ያውቁ ነበር፣ እናም ስለዚህ ከእነርሱ ጋር ለመገናኘት ተዘጋጁ፤ አዎን በጎራዴም፣ በሻሙላም፣ በሰይፍ፣ በቀስትም፣ በድንጋይና በወንጭፍ፣ እናም በሁሉም ዓይነት [ሀ]የጦር መሳሪያዎች ከሁሉም ዓይነት እራሳቸውን አስታጠቁ።

፲፫ እናም በሚመጡበት ጊዜ አምሊኪ

፪ ፩ሀ አልማ ፩፥፰።
፫ሀ ሞዛያ ፳፱፥፳፮–፳፯፤ አልማ ፬፥፲፯።
፬ሀ አልማ ፲፥፲፱፤ ሔለ. ፭፥፪።
፭ሀ ፫ ኔፊ ፲፩፥፳፱።
፲፩ሀ አልማ ፫፥፬።
ለ ያዕቆ. ፩፥፲፫–፲፬፤ ሞዛያ ፳፭፥፲፪፤ አልማ ፫፥፲፩።
፲፪ሀ ሞዛያ ፲፥፰፤ ሔለ. ፩፥፲፬።

ውያንን ለመገናኘት እንደዚህ ተዘጋጅተው ነበር። እናም እንደብዛታቸው አምበሎችና፣ ከፍተኛ የቡድን አለቆች፣ እንዲሁም የበ ላይ ሻምበሎች ተሹመው ነበር።

፲፬ እናም እንዲህ ሆነ አምሊኪ ከሁሉም ዓይነት የጦር መሳሪያዎች ህዝቡን አስታ ጥቆ ነበር፤ እናም ደግሞ ከወንድሞቻቸው ጋር ለማዋጋት እንዲመሩአቸው ገዥዎች ንና መሪዎችን በህዝቡ ላይ ሾመ።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ አምሊካውያኑ ወደ ᵐዛራሄምላ ምድር በሚፈሰው ᵃበሲዶም ወንዝ በስተምስራቅ በኩል ባለው በአምኒሁ ኮረብታ ላይ ሆኑ፣ እናም ከኔፋውያን ጋር ጦርነት ጀመሩ።

፲፮ እንግዲህ አልማ የኔፋውያን ᵐዋና ዳኛ እናም የህዝቡ አስተዳዳሪ በመሆኑ፣ ከህዝቡ ጋር አዎን ከሻምበሎቹ ጋር፣ እናም ከበላይ ሻምበሎቹ ጋር አዎን ከወታደሮቹ ፊት በመ ሆን ከአምሊኪውያን ጋር ለመዋጋት ሄደ።

፲፯ እናም በሲዶም በስተምስራቅ ኮረብታ ላይ አምሊኪውያንን መግደል ጀመሩ። እናም አምሊኪውያን በታላቅ ብርታት በር ካታ ኔፋውያን ከአምሊኪውያን ፊት እስኪ ወድቁ ከኔፋውያን ጋር ተዋጉ።

፲፰ ይሁን እንጂ ጌታ በታላቅ ግድያ አምሊኪውያን እንዲገደሉ የኔፋውያ ንን ክንድ አበረታ፤ እነርሱም ከፊታቸው መሸሽ ጀመሩ።

፲፱ እናም እንዲህ ሆነ ኔፋውያን በዚያን ቀን ሁሉ አምሊኪውያንን ተከተሉ፣ እናም አስራ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ሠላሣ ሁለት አምሊኪውያንን ነፍስ እስኪገደሉ ድረስ በታላቅ ግድያ ᵐገደሉአቸው፤ እናም ስድ ስት ሺህ አምስት መቶ ስልሳ ሁለት የኔፋ ውያን ነፍስ ጠፍተው ነበር።

፳ እናም እንዲህ ሆነ አልማ ምንም እን ኳን አምሊኪውያንን ለማሳደድ በማይች ልበት ጊዜ፣ ᵐበኔሆር እጅ በጎራዴ በተገ ደለው በጌዲዮን ስም በተሠየመ ሸለቆው፣ ᵃበጌዴዎን ሸለቆ ህዝቡ ድንኳናቸውን እን ዲተክሉ አደረገ፤ እናም በዚህ ሸለቆ ኔፋው ያን ለምኗት ድንኳናቸውን ተክለው ነበር።

፳፩ እናም አልማ የአምሊኪውያንን ዕቅ ድና ሴራ ያውቅ ዘንድ፣ በዚያም እራሱን ከእነርሱ ይጠብቅ ዘንድ፣ ህዝቡንም ከጥ ፋት ይጠብቅ ዘንድ ቅሪቶቻቸውን ለመከ ታተል ሰላዮችን ላከ።

፳፪ አሁን የአምሊኪውያንን የጦር ሰፈር እንዲመለከቱ የላካቸው ዜራምና፣ አምኖ ርም፣ ማንቲና ሊምኸር ተብለው ይጠ ራሉ፤ እነዚህ የአምሊኪውያንን የጦር ሰፈር እንዲመለከቱ ከወንድ ሰዎቻቸው ጋር የሄ ዱት ናቸው።

፳፫ እናም እንዲህ ሆነ በማግስቱ ወደ ኔፋ ውያን የጦር ሰፈር በችኮላ ተመለሱ፣ በኃ ይል በመገረም እናም በታላቅ ፍርሃት እን ዲህ አሉ፥

፳፬ እነሆ ᵐየአምሊኪውያንን የጦር ሰፈር ተከተልን፣ በሚኖን ምድር ከዛራሄምላ ምድር ከፍ ብሎ ወደ ᵃኔፊ ምድር በሚ ወስደው በርካታ የላማናውያን ሰራዊቶችን ተመለከትን፤ እናም እነሆ አምሊኪውያን እነርሱን ተገናኙአቸው፤

፳፭ እናም በምድሪቱ በወንድሞቻችን ላይ ናቸው፤ እናም ከመንጋዎቻቸውና፣ ከሚ ስቶቻቸው፣ እናም ከልጆቻቸው ጋር ወደ እኛ ከተማ እየሸሹ ናቸው፤ እናም እኛ ካል ፈጠንን በስተቀር ከተማችንን ይወስዱብ ናል፣ እናም አባቶቻችንና ሚስቶቻችን እን ዲሁም ልጆቻችን ይገደላሉ።

፳፮ እናም እንዲህ ሆነ የኔፊ ህዝብ ድን ኳናቸውን ወሰዱ፣ እናም ከጌዴዎን ሸለቆ ወጥተው ᵐየዛራሄምላ ከተማ ወደ ነበረው ወደ ራሳቸው ከተማ ሄዱ።

፳፯ እናም እነሆ፣ የሲዶምን ወንዝ ባቋ ረጡበት ጊዜ እንደ ባህር አሸዋ ᵐቁጥራቸው

፲፭ ᵘ አምኒ ፩፡፲፫–፲፭።
ᵛ አልማ ፫፡፫።
፲፮ ᵘ ሞዛያ ፳፱፡፴፪።
፲፱ ᵘ አልማ ፫፡፩–፪፣ ፳፯፣ ፴፡፪።

፳ ᵘ አልማ ፩፡፯–፲፭፣ ፲፰፡፲፯።
ᵛ አልማ ፯፡፯።
፳፩ ᵘ አልማ ፫፡፣ ፴፡ ፲፫–፲፳።
ᵛ ፪ ኔፊ ፭፡፳።

፳፯ ᵘ አምኒ ፩፡፲፰፣ ፲፳።
፳፯ ᵘ ጄረም ፩፡፯።

የበዛ የሚመስሉት ላማናውያንና አምሊኪ ውያን ሊያጠፉአቸው መጡ።

፳፯ ይሁን እንጂ ኔፋውያን በጌታ ክንድ ᵛብርታትን በማግኘታቸው እርሱ ከጠላ ቶቻቸው እጅ ያስለቅቃቸው ዘንድ በኃ ይል ፀለዩ፤ ስለዚህ ጌታ ጩኸታቸውን ሰማና አበረታቸው፣ እናም ላማናውያንና አምሊኪውያን በፊታቸው ወደቁ።

፳፱ እናም እንዲህ ሆነ አልማ ከአምሊኪ ጋር በጎራዴ ፊት ለፊት ተፋለመ፣ እናም እርስ በእርሳቸው በኃይል ተጣሉ።

፴ እናም እንዲህ ሆነ አልማ የእግዚአብ ሔር ሰው በመሆኑ፣ ᵛበእምነትም የተነሳሳ በመሆኑ እንዲህ በማለት ጮኸ፥ አቤቱ ጌታ ምህረትህ በእኔ ላይ ይሁን እናም ነፍሴን አት ርፍ፣ እኔም ይህንን ህዝብ አድነውና እጠብ ቀው ዘንድ በእጅህ መሳሪያ እሆን ዘንድ።

፴፩ አሁን አልማ እነዚህን ቃላት በተና ገረ ጊዜ ከአምሊኪ ጋር እንደገና ታገለ፤ አምሊኪን በጎራዴ እስኪገድለውም በር ትቶ ነበር።

፴፪ እናም ደግሞ እርሱ ከላማናውያን ንጉስ ጋር ታግሎ ነበር፤ ነገር ግን የላማና ውያን ንጉስ ከአልማ ፊት ሸሸ እናም ከአ ልማ ጋር እንዲታገሉ ጠባቂዎቹን ላከ።

፴፫ ነገር ግን አልማ ከጠባቂዎቹ ጋር፣ ከላማናውያን ንጉስ ጠባቂዎች ጋር እነርሱን በመግደል እስኪመልሳቸው ድረስ ተዋጋ።

፴፬ እናም የተገደሉትን የላማናውያንን ሬሳ በሲዶም ወንዝ በመጣል፣ ህዝቡም ከላ ማናውያንና ከአምሊኪውያን ጋር በሲዶም ወንዝ በስተምዕራብ በኩል በማቋረጥ እን ዲዋጉ ቦታ ይኖራቸው ዘንድ ቦታውን በሌላ አነጋገር ከሲዶም ወንዝ በስተምዕ ራብ በኩል ያለውን ዳርቻ እንደዚህ አጠራ።

፴፭ እናም እንዲህ ሆነ ሁሉም የሲዶምን ወንዝ ባቋረጡ ጊዜ፣ ምንም እንኳን እጅግ ብዙ ሆነው ለመቁጠር የማይቻል ቢሆኑም ላማናውያንና አምሊኪውያን ከፊታቸው መሸሽ ጀመሩ።

፴፮ እናም ከምድሪቱ ዳርቻ በስተምዕራ ብና በስተሰሜን በኩል ወዳለው ምድረበዳ ከኔፋውያን ፊት ሸሹ፤ እናም ኔፋውያን በኃይላቸው አሳደዱአቸውና ገደሉአቸው።

፴፯ አዎን፣ በየአቅጣጫው ተገናኙአ ቸው፤ እናም በምዕራብና በሰሜን በኩል እስኪበተኑ ድረስ በስተሰሜን በኩል ሔርማውንትስ ከሚባለው ስፍራ በምድ ረበዳው እስከሚደርሱ ድረስ አባረሩአቸው እናም ገደሉአቸው፤ እና ይህም በዱርና በስግብግብ አውሬዎች የተወረረው ምድ ረበዳ ክፍል ነበር።

፴፰ እናም እንዲህ ሆነ ብዙዎች በቁስላ ቸው በምድረበዳው ሞቱና፣ በአውሬዎ ቹና ደግሞ በጥንብ አንሳዎች ተበሉ፤ እናም አጥንታቸው በምድር ላይ ተቆልሎ ተገኘ።

ምዕራፍ ፲

አምሊኪውያን እንደ ትንቢቱ ቃል እራሳ ቸው ላይ ምልክት አደረጉ—ላማናውያን በአመፃቸው ተረገሙ—ሰዎች እርግማና ቸውን በላያቸው ላይ ያመጣሉ—ኔፋው ያን ሌሎች የላማናውያንን ሠራዊት አሸ ነፉ። ከ፹፯–፹፱ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ በጦር መሳሪያ ᵛያል ተገደሉት ኔፋውያን የተገደሉትን ከቀበሩ በኋላ፣ የሞቱት ቁጥር ብዙ ስለነበሩ ለመ ቁጠር አይቻልም ነበር፣ የሞቱትን ከቀበሩ በኋላ በሙሉ ወደ ስፍራቸው እናም ወደ ቤታቸውና ወደ ሚስቶቻቸውና ወደ ልጆ ቻቸው ተመለሱ።

፪ አሁን ብዙ ሴቶችና፣ ልጆች፣ ደግሞም ብዙ መንጋና፣ ከብቶቻቸው በጎራዴ ተገ ድለውባቸው ነበር፤ እናም ደግሞ በርካታ የእህል እርሻዎቻቸው ወድመዋል፣ በሰዎች ሰራዊት ተረጋግጠውባቸዋልና።

፫ እናም አሁን በሲዶም ወንዝ ዳርቻ የተ ገደሉት ላማናውያንና አምሊኪውያን ሁሉ ᵛበሲዶም ወንዝ ውስጥ ተጥለው ነበር፤

፳፯ᵛ ዘዳግ. ፴፩፡፮። ᵛ ፩ᵛ አልማ ፪፡ ፲፱፣ ፴፡ ፪።
፴ᵛ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን። ᵛ ᵛ አልማ ፪፡ ፲፭።

እናም እነሆ በርካታ አጥንቶች ^በባህር ወለል ውስጥ ናቸው፣ እነርሱም ብዙ ናቸው።

፬ እናም ^አምሊኪውያን እንደላማናውያን ግንባራቸው ላይ ^ቀይ ምልክት በማድረጋ ችው ከኔፋውያን ተለይተው ነበር፤ ይሁን እንጂ እንደላማናውያን ራሳቸው እንዲላጭ አላደረጉም።

፭ እንግዲህ የላማናውያን ራስ ተላጭቶ ነበር፣ እናም ከታጠቁት ቆዳና ደግሞ ከታ ጠቁት የጦር መሳሪያና፣ ጦርና፣ ቀስትና፣ ድንጋይና፣ ወንጭፍና ሌሎች ተመሳሳይ ነገሮች በስተቀር ^እርቃናቸውን ነበሩ።

፮ እናም አባቶቻቸው በኔፊ፣ በያዕቆብ፣ በዮሴፍ፣ እናም በሳም ፍፁምና ቅዱስ በሆኑት ወንድሞቻቸው ላይ በመተላለፋ ቸውና፣ በማመፃቸው ምክንያት ^በእርግ ማን በተደረገባቸው ምልክት መሰረት የላ ማናውያን ቆዳ ጥቁር ነበር።

፯ እናም ወንድሞቻቸው ሊያጠፉአቸው ፈለጉ፤ ስለሆነም እነርሱ የተረገሙ ሆኑ፤ እናም ጌታ እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ፣ አዎን፣ በላማንና በልሙኤል፣ ደግሞም በእስማኤል ልጆችና፣ በእስማኤላውያን ሴቶች ላይ ^ምልክትን አደረገባቸው።

፰ እናም ይህ የተደረገው ዘሮቻቸው ከወ ንድሞቻቸው ዘሮች ጋር እንዲለዩ፣ ጥፋታ ቸውን ከሚያረጋግጠው ^ከተሳሳተው ባህል ጋር ራሳቸው ^እንዳይቀላቅሉና እንዳያምኑ ጌታ እግዚአብሔርም ይጠብቃቸው ዘንድ ነው።

፱ እናም እንዲህ ሆነ ዘሩን ከላማናውያን ጋር የቀላቀለ ማንኛውም በዘሩ ላይ ተመሳ ሳይ እርግማንን ያመጣል።

፲ ስለዚህ በላማናውያን መመራት የፈለገ ማንኛውም በስሙ ይጠራል፣ እናም በላዩ ላይም ምልክት ይደረግበታል።

፲፩ እናም እንዲህ ሆነ ^በላማናውያን ባህል የማያምን ነገር ግን፣ ከኢየሩሳሌም ምድር የመጡትን ታሪኮች፣ እናም የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ባመኑትና እነርሱን በሚጠበቁት፣ ደግሞ ትክክል በሆኑት፣ የአባቶቻቸውን ባህል የሚያምኑ ማንኛቸውም ከዚህ ጊዜ በኋላ ኔፋውያን ወይንም የኔፊ ህዝብ ተብ ለው ተጠርተዋል—

፲፪ እናም ^እውነት የሆነውን የህዝባቸ ውን፣ እናም ደግሞ የላማናውያንን ሰዎች ታሪክ ያስቀመጡት እነርሱ ናቸው።

፲፫ አሁን ወደ አምሊኪውያን እንደ ገና እንመለሳለን፣ በእነርሱም ላይ ደግሞ ^ምልክት ተደርጎባቸዋልና፤ አዎን፣ በራ ሳቸውም ላይ ምልክት፣ አዎን፣ በግንባራ ቸው ላይ ቀይ ምልክት አድርገዋል።

፲፬ ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል ተፈፅ ሟል፤ ለኔፊ የተናገራቸው ቃላት እነዚህ ናቸውና፥ እነሆ፣ ላማናውያንን ረግሜአ ለሁ፣ እናም ለኃጢአታቸው ንስሃ ካልገ ቡና፣ ምህረትን እንዳደርግላቸው ዘንድ ወደ እኔ ^ካልተመለሱ በስተቀር፣ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እስከ ዘለዓለም እነርሱም ሆኑ ዘሮቻቸው ከአንተ ከዘሮችህ ይለዩ ዘንድ ምልክት አደርግባቸዋልሁ።

፲፭ እናም በድጋሚ፥ ዘሩን ከወንድሞችህ ጋር የደባለቀውን በላዩ ላይ ምልክትን አደ ርጋለሁ፣ እነርሱም ደግሞ የተረገሙ ይሆኑ ዘንድ።

፲፮ እናም በድጋሚ ከአንተና ከዘሮችህ ጋር የተጣላውን ምልክት አደርግበታለሁ።

፲፯ እናም በድጋሚ፣ ከአንተ የተለየም ከእንግዲህ የአንተ ዘር ተብሎ አይጠራም፣ አንተንና የአንተ ዘር ተብሎ የሚጠራውን ሁሉ ከአሁን ጀምሮ እስከ ዘለዓለም እባርካ ለሁ፤ እናም እነዚህም ለኔፊና ለዘሮቹ የጌታ ቃል ኪዳን ነበሩ።

፲፰ አሁን አምሊኪውያን በግንባራቸው

፫ ለ አልማ ፸፬፡፳፪።
፬ ሀ አልማ ፪፡፲፩።
ለ አልማ ፫፡፲፫–፲፱።
፭ ሀ ኢኖስ ፩፡፳፣ ሞዛያ ፲፡፳፣ አልማ ፸፪፡፲፳–፳፩።
፮ ሀ ፪ ኔፊ ፭፡፳፩፣ ፳፯፡፴፫።
ቅ.መ.መ. እርግማን፣ እርግማኖች።
፯ ሀ ፩ ኔፊ ፲፪፡፳፫።
፰ ሀ ሞዛያ ፲፡፲፩–፲፳፣ አልማ ፱፡፲፯።
ለ ቅ.መ.መ. ጋብቻ፣ መጋባት—በሀይማኖቶች መካከል መጋባት።
፲፩ ሀ አልማ ፲፯፡፱–፲፩።
፲፪ ሀ ሞዛያ ፩፡፯፣ ኤተር ፪፡፯–፲፩።
፲፫ ሀ አልማ ፫፡፪።
፲፬ ሀ ፪ ኔፊ ፴፡፪–፯።

ላይ ምልክት ማድረግ ሲጀምሩ የእግዚአብ ሔር ቃል እንደተፈፀመ አያውቁም ነበር፤ ይሁን እንጂ በግልፅ ከእግዚአብሔር ጋር ᵐለአመፃ መጡ፤ ስለዚህ እርግማኑ በእነ ርሱ ላይ መሆኑ አስፈላጊ ነበር።

፲፤፪ እንግዲህ ᵐእርግማኑን በራሳቸው ላይ እንዳመጡት እንድትረዱ እፈልጋለሁ፤ እናም የተረገመ ሰውም እርግማኑን በራሱ ላይ ያመጣል።

፳ አሁንም እንዲህ ሆነ በላማናውያንና በአምሊኪውያን በዛራሄምላ ምድር ከተ ደረገው ውጊያ በኋላ ብዙ ቀንም ሳይቆይ፣ የመጀመሪያው ሠራዊት አምሊኪውያንን ባገኘበት ᵐቦታ በኔፊ ህዝብ ላይ ሌሎች የላ ማናውያን ሠራዊት መጡ።

፳፩ እናም እንዲህ ሆነ እነርሱን ከምድራ ቸው ለማስለቀቅ ወታደሮች ተላኩ።

፳፪ እንግዲህ አልማ ᵐበቁስሉ በመሰቃ የቱ በዚህ ጊዜ ከላማናውያን ጋር ለመዋ ጋት አልሄደም ነበር፤

፳፫ ነገር ግን ብዙ ወታደሮችን ላከባ ቸው፤ እናም ሄደው በርካታ ላማናውያኖ ችን ገደሉ፣ እናም የቀሩትን ከድንበራቸው ነድተው አስወጡአቸው።

፳፬ እናም ከዚያ በኋላ ለጊዜው በጠላቶቻ ቸው ስለማይቸገሩ በድጋሚ ወደ ምድራ ቸው ተመልሰው ሰላምን መመስረት ጀመሩ።

፳፭ አሁን እነዚህ ሁሉ ነገሮች የሆኑት፣ አዎን፣ እነዚህ ሁሉ ጦርነቶችና ፀቦች የተ ጀመሩትና የተፈፀሙት በመፃፍንቱ በአ ምስተኛው ዓመት የንግስ ዘመን ነበር።

፳፮ እናም ዘለዓለማዊ ደስታን፣ ወይም ዘለአለማዊ ስቃይን እንዲቀበሉ፣ እንደታ ዘዙለት መንፈስ እንደሰራቸው፣ መልካ ምም ይሁን መጥፎ ᵐዋጋቸውን ያገኙ ዘንድ በአንድ ዓመት ውስጥ ሺህ እናም አስር ሺህ ነፍስ ወደ ዘለአለማዊ ዓለም ተላኩ።

፳፯ ማንኛውም ሰው ᵐበመታዘዝ በሰማው ᵃደመወዙን ይቀበላል፣ እናም ይህ እንደ ትንቢቱ መንፈስ ቃል መሰረት ነው፤ ስለ ዚህ እንደ እውነቱ ይሁን። እናም የመሳ ፍንቱ የአምስተኛ ዓመት አገዛዝ እንደዚህ ተፈፀመ።

ምዕራፍ ፩

አልማ በሺህዎች የሚቆጠሩ የተለወጡትን አጠመቀ—ክፉት በቤተክርስቲያኗ ውስጥ ገባ፣ እናም የቤተክርስቲያኗ እድገት ተገታ—ኔፊያህ ዋና ዳኛ ሆኖ ተሾመ—አልማ ሊቀ ካህን በመሆኑ ራሱን ለአገልግ ሎት ሰጠ። ከ፹፯–፹፫ ዓ.ዓ. ገደማ።

፩ እንግዲህ እንዲህ ሆነ በኔፊ ህዝብ ላይ በመፃፍንቱ ስድስተኛ ዓመት የንግስ ዘመን፣ ᵐበዛራሔምላ ምድር ምንም ዓይ ነት ፀብና ጦርነት አልነበረም።

፪ ነገር ግን ህዝቡ ተሰቃይቶ ነበር፣ አዎን፣ ᵐወንድሞቻቸው ስለሞቱባቸው፣ እናም ደግሞ ከብቶቻቸውንና መንጋዎቻቸውን በማጣታቸው፣ እናም ደግሞ የመስኮቻቸው እህሎች በእግር በመረገጡና በላማናውያን ስለጠፉባቸው እጅግ ተሰቃዩ።

፫ እናም ስቃያቸው ታላቅ ሆኖ ሁሉም ነፍስ የሚያዝኑበት ምክንያት ነበራቸው፤ እናም ይህ የእግዚአብሔርን ፍርድ በኃጢ አታቸውና በእርኩሰታቸው የተነሳ በላያ ቸው ላይ በእግዚአብሔር የተላከ ቁጣ እን ደሆነ ያምኑ ነበር፤ ስለሆነም ሀላፊነታቸውን ለማስታወስ ነቅተው ነበር።

፬ እናም ቤተክርስቲያኗን ይበልጥ ሙሉ በማድረግ ማቋቋም ጀመሩ፤ አዎን፣ እናም ብዙዎች በሲዶም ወንዝ ᵐተጠመቁ እናም የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን አባል ሆኑ፤ አዎን፣ በቤተክርስቲያኗ ሰዎች ላይ ᵃሊቀ

፲፯ ᴴ ፬ ኔፊ ፭፡ ፴፯።
ቅ.መ.መ. አመጽ።
፲፱ ᴴ ፪ ኔፊ ፭፡ ፳፩–፳፭፤
አልማ ፲፯፡ ፲፭።
፳ ᴴ አልማ ፪፡ ፳፬።
፳፪ ᴴ አልማ ፪፡ ፳፱–፴፫።
፳፭ ᴴ ቅ.መ.መ. ስራዎች።
፳፯ ᴴ ሮሜ ፮፡ ፲፮፤
ሔለ. ፲፬፡ ፳፱–፴፩።
ቅ.መ.መ. ታዛዥነት፣
ታዛዥ፣ መታዘዝ።
ᵃ ሞዛያ ፪፡ ፴፩–፴፫፤
አልማ ፭፡ ፶፩–፶፪።
፩ ᴴ ፩ ᴴ ኦምኒ ፩፡ ፲፪–፲፱።
፪ ᴴ አልማ ፪፡ ፲፱፤
፫፡ ፩–፪፣ ፳፯።
፬ ᴴ ሞዛያ ፲፰፡ ፲–፲፯።
ᵃ ሞዛያ ፳፱፡ ፶፪።

ካህን በመሆን በአባቱ በአልማ በተሾመው በአልማ እጅ ተጠመቁ።

፮ እናም እንዲህ ሆነ በመሣፍንቱ በሰባ ተኛው ዓመት የንግስ ዘመን ወደ ሶስት ሺህ አምስት መቶ ነፍሳት በእግዚአብሔር ᵐቤተ ክርስቲያን ራሳቸውን አባል ያደረጉና የተ ጠመቁ ነበሩ። እና እንደዚህም በኔፊ ህዝብ የነገሱበት ሰባተኛው የመሳፍንቱ የአገዛዝ ዘመን ተፈጸመ፤ እናም በጊዜውም ሁሉ ዘላቂ ሰላም ነበር።

፯ እናም እንዲህ ሆነ በመሣፍንቱ ስምን ተኛው ዓመት የንግስ ዘመን፣ የቤተክርስ ቲያኗ ሰዎች በአስደናቂው ᵐሀብቶቻቸውና፣ ᵃበመልካሙ ሐሮቻቸውና፣ በተፈተለ ጥሩ በፍታና፣ በብዙ መንጋዎቻቸውና፣ ወርቃ ቸውና፣ ብራቸው፣ እናም በከበሩ ነገሮቻ ቸው ሁሉ መኩራት ጀመሩ፤ እናም በእነ ዚህ ነገሮች ሁሉ በኩራት ተወጠሩ፣ ውድ ልብሶችን መልበስ ጀምረዋልና።

፰ እንግዲህ ይህ ለአልማ፣ አዎን፣ እናም አልማ በቤተክርስቲያኗ ላይ መምህራንና ካህናት፣ እናም ሽማግሌዎች አድርጎ ᵐለቀ ባቸው ሰዎች ታላቅ ስቃይ መንስኤ ነበር፤ አዎን፣ ብዙዎች በህዝባቸው መካከል ሲጀ መር ስለተመለከቱት ኃጢኣትም በምሬት አዘኑ።

፱ የቤተክርስቲያኗ ሰዎች ᵐበኩራት ዐይን የተነሳሱና፣ ልባቸውን በሀብት፣ እና በዓ ለም ከንቱ ነገሮች ላይ ያሳረፉ፣ አንደኛው ሌላኛውን መውቀስ በመጀመራቸውና እንደ ፍቃዳቸውና ፍላጎታቸው ᵃያላመኑ ትን ማሳደድ በመጀመራቸው በታላቅ ሀዘን አይተውታል እናም ተመልክተውታልና።

፲ እናም በመሣፍንቱ ስምንተኛ የንግስ ዘመን በቤተክርስቲያኗ ሰዎች መካከል ታላቅ ᵐፀብ ተጀመረ፤ አዎን፣ ᵃምቀኝነትና ፀብ፣ እናም ተንኮልና፣ ስደትና ኩራት፣ እንዲሁም ከእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ካልሆኑት የሚበልጥ ኩራት ነበር።

፲፩ እናም ስምንተኛው የመሣፍንት የንግስ ዘመን ተፈጸመ፤ እናም የቤተክርስቲያኗ ኃጢያት በቤተክርስቲያኗ አባል ላልሆኑት ታላቅ የመሰናከያ አለት ነበር፤ እናም ቤተ ክርስቲያኗ ከዕድገቷ መገታት ጀመረች።

፲፪ እናም እንዲህ ሆነ በዘጠነኛው ዓመት መጀመሪያ፣ አልማ የቤተክርስቲያኗን ኃጢያት ተመለከተ፣ እናም የቤተክርስ ቲያኗ አባላት ᵐምሳሌም አማኝ ያልሆኑት ከአንዱ ክፋት ወደሌለኛው ሲመራቸው፣ በዚህም ህዝቡን ወደጥፋታቸው ሲያመጣ ቸው ተመለከተ።

፲፫ አዎን፣ በህዝቡ መካከል ታላቅ አድል ዎን ተመለከተ፣ አንዳንዶች ሌሎችን በመ ጥላት፣ ᵐበተቸገሩና በተራቆቱ እንዲሁም ᵃበተራቡ፣ እናም በተጠሙትና፣ በታመ ሙትና በተሰቃዩት ላይ ጀርባቸውን በመ ስጠት ራሳቸውን በክፋት ከፍ አደረጉ።

፲፬ እንግዲህ ይህ በህዝቡ መካከል የለቅሶ አቸው ታላቅ ምክንያት ነበር፣ ሌሎች እራ ሳቸውን ሲያዋርዱ፣ ከንብረቶቻቸው ለድ ሆችና ለተቸገሩት ᵐበማካፈል፣ የተራቡ ትን በመመገብ እርዳታ ማግኘት ለሚፈ ልጉ እርዳታን በማድረግ፣ እናም እንደት ንቢቱ መንፈስ መምጣት ላለበት ክርስቶስ ᵃሲሉም በሁሉም ዓይነት ᶜስቃይ ተሰቃዩ፤

፲፭ ያንን ቀን በመጠባበቅ ᵐኃጢኣታቸውን መሰረያ እንዲህ አገኙ፤ በኢየሱስ ክርስቶስ ፈቃድና ኃይል መሰረት ከሞት እስር በመላ ቀቅ በሙታን ትንሣኤ በታላቅ ᵃደስታ ተሞ ልተው ነበር።

፲፮ እናም አሁን እንዲህ ሆነ አልማ ትሁት የእግዚአብሔር ተከታዮችን ስቃይ በመ

፮ ሀ ሞዛያ ፳፭፡ ፲፳–፳፫፤ ፫ ኔፊ ፳፯፡ ፳፩።
፯ ሀ ቅ.መ.መ. ሀብቶች።
ለ አልማ ፩፡ ፳፱።
፯ ሀ ቅ.መ.መ. ስልጣን።
፰ ሀ ቅ.መ.መ. ከንቱ፣ ከንቱነት፤ ኩራት።
ለ አልማ ፩፡ ፳፩።
፱ ሀ ቅ.መ.መ. ጸብ።
ለ ቅ.መ.መ. ቅናት።
፲፩ ሀ ፪ ሳሙ. ፲፪፡ ፲፱፤ አልማ ፴፱፡ ፲፩።
፲፪ ሀ ኢሳ. ፫፡ ፲፱፤ ያዕቆ. ፪፡ ፲፯።
ለ ሞዛያ ፱፡ ፳፯።
፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. ምፅዋት፣ የምፅዋት ስጦታ።
ለ ቅ.መ.መ. ጭንቀት።
ሐ ፪ ቆሮ. ፲፪፡ ፣።
፲፬ ሀ ሞዛያ ፬፡ ፲፪፤ አልማ ፭፡ ፳፯–፴፭። ቅ.መ.መ. ማፅደቅ፣ ከበደል ነጻ መሆን።
ለ ቅ.መ.መ. ደስታ።

መልከቱ፣ እናም በተቀሩት ሰዎች ስደት የተነሳና፣ [ሀ]ክፋታቸውን ሁሉ በመመልከቱ እጅግ ማዘን ጀመረ፤ ይሁን እንጂ የጌታ መንፈስ አልተወውም።

፲፯ እናም ከቤተክርስቲያኗ ሽማግሌዎች መካከል አንድ ብልህ ሰው መረጠ፣ እናም ለእርሱ በተሰጠው [ለ]ህግ መሰረትና በህዝቡም ላይ እንደክፋታቸውና እንደ ወንጀላቸው ያስፈፅም ዘንድ [ሐ]በህዝቡ ድምፅ መሠረት ሥልጣንን ሰጠው።

፲፰ እንግዲህ የዚህ ሰው ስም ኔፊያህ ነበር፣ እናም እርሱ [መ]ዋና ዳኛ በመሆን ተመድቦ ነበር፤ እናም በፍርድ ወንበር ህዝቡን እንዲዳኝና እንዲገዛ ተቀመጠ።

፲፱ እንግዲህ አልማ በቤተክርስቲያኗ ላይ ሊቀ ካህን እንዲሆን ስልጣን አልሰጠውም፤ ነገር ግን የሊቀ ካህንነቱን ሀላፊነት ለራሱ ያዘው፤ ይሁን እንጂ የፍርዱን ወንበር ለኔፊያህ ሰጥቶታል።

፲፱ እናም ይህን ያደረገው በህዝቡ መካከል [ሀ]እራሱ ይጓዝ ወይም በኔፊ ህዝብ መካከል [ለ]የእግዚአብሔርን ቃል ይሰብክ ዘንድ፣ ስራቸውን [ሐ]እንዲያስታውሱ እነርሱን [መ]ለማነሳሳት እናም በእግዚአብሔር ቃል ኩራታቸውንና ተንኮላቸው፣ እናም በህዝቡ መካከል ያለውን ፀብ ጎትቶ ለማስወረድ ነበር፣ በእነርሱ ላይ ንጹሁን [ሠ]ምስክር በግድ ከመገፋፋት በስተቀር እነርሱን መልሶ የሚያገኝበት ሌላ መንገድ እንደሌለ ተመልክቶ ነበር።

፳ እናም በኔፊ ህዝብ ላይ በዘጠነኛው ዓመት የመሣፍንቱ አገዛዝ መጀመሪያ አልማ የፍርዱን ወንበር [ሀ]ለኔፊያህ እንዲህ ሰጠው፣ እናም እራሱንም ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ቅዱሱ ስርዓት [ለ]ታላቅ ክህነት በራዕይና ትንቢት መንፈስ መሰረት በቃል ምስክርነት ላይ እራሱን ወሰነ።

በእግዚአብሔር ቅዱሱ ስርዓት መሰረት ሊቀ ካህኑ የነበረው አልማ ለህዝቡ በከተማቸውና በምድሪቱ ባሉት መንደሮች በሙሉ የተናገረው ቃል።

ከምዕራፍ ፭ ጀምሮ።

ምዕራፍ ፮

ደህንነት ለማግኘት ሰዎች ንስሀ መግባትና ትዕዛዛቱን መጠበቅ፣ ዳግም መወለድ፣ በክርስቶስ ደም ልብሳቸውን ማፅዳት፣ ትሁት መሆንና፣ ከኩራትና ከምቀኝነት እራሳቸውን ማስወገድ እናም የፅድቅን ስራ መስራት አለባቸው—መልካሙ እረኛ ህዝቡን ይጠራል—ክፉ ስራ የሚሰሩ የዲያብሎስ ልጆች ናቸው—አልማ የት ምህርቱን እውነተኛነት መሰከረ፣ እናም ሰዎች ንስሀ እንዲገቡ አዘዘ—የፃድቃኖች ስም በህይወት መዝገብ ይፃፋል። በ፳፻፲ ም.ዓ. ገደማ።

፩ አሁን እንዲህ ሆነ አልማ በመጀመሪያ በዛራሔምላ ምድር እናም ከዚያም በምድሪቱ ላይ ሁሉ ለህዝቡ [ሀ]የእግዚአብሔርን ቃል [ለ]መናገር ጀመረ።

፪ እናም በእርሱ አመዘጋገብ መሠረት በዛራሔምላ ከተማ ለተመሰረተችው ቤተክርስቲያን ሰዎች የተናገራቸው ቃላት እነዚህ ናቸው።

፫ እኔ አልማ በአባቴ በአልማ በእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ላይ [ሀ]ሊቀ ካህን በመሆን [ለ]በመቀባቴ፤ እርሱም ከእግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች ለመፈፀም ኃይልና [ሐ]ስልጣን ስላለው፣ እነሆ፣ እላችኋላሁ፣ እርሱም በኔፊ [መ]ምድር ወሰን ላይ ቤተክርስቲያንን ማቋቋም ጀመረ፤ አዎን፣ የሞርሞን ምድር

፲፭ [ሀ] ት. እና ቃ. ፴፯፡፴፯፤ ፵፱፡፳።
፲፮ [ሀ] አልማ ፩፡፩፣ ፲፬፣ ፲፯።
[ለ] አልማ ፪፡፫–፯።
፲፯ [ሀ] አልማ ፶፡፴፯።
፲፱ [ሀ] አልማ ፯፡፩።
[ለ] አልማ ፴፩፡፭፤
ት. እና ቃ. ፲፩፡፳፩–፳፪።
[ሐ] ሞዛያ ፩፡፲፯፤
ሔለ. ፲፪፡፫።
[መ] ኢኖስ ፩፡፳፫።
[ሠ] ቅ.መ.መ. ምስክርነት።
፳ [ሀ] አልማ ፳፡፲፪።
[ለ] ሞዛያ ፳፱፡፵፪፤
አልማ ፭፡፫፣ ፵፬፣ ፵፱።
፲፭ [ሀ] አልማ ፭፡፳፩።
[ለ] አልማ ፬፡፲፱።
፲ [ሀ] አልማ ፬፡፬፣ ፲፰፣ ፳፡ ፲፡ ፲፡ ፳።
[ለ] ቅ.መ.መ. መሾም፣ ሹመት።
[ሐ] ሞዛያ ፲፡ ፲፣ ፲፡ ፲ ኔፊ ፲፩፡ ፳፭።
[መ] ሞዛያ ፲፡ ፲፡ ፲ ኔፊ ፭፡ ፲፪።
[ለ] አልማ ፬፡ ፲፱።
፲ [ሀ] አልማ ፬፡ ፬፡ ፲ ፡ ፲ ፡ ፳።
[ለ] ቅ.መ.መ. መሾም፣ ሹመት።
[ሐ] ሞዛያ ፲ ፡ ፲ ፣ ፲ ፡ ፲ ኔፊ ፲ ፡ ፳ ፡ ፳ ።
[መ] ሞዛያ ፲ ፡ ፲ ፣ ፲ ኔፊ ፭ ፡ ፲ ።

ተብላ በምትጠራው ምድር ላይ፤ አዎን፣ እናም በሞርሞን ውሃ ወንድሞቹን አጠመ ቃቸው።

፮ እናም እነሆ፣ እላችኋለሁ፣ እነርሱ ከን ጉስ ኖህ ሰዎች እጅ በእግዚአብሔር ኃይ ልና ምህረት ᵐድነው ነበር።

፯ እናም እነሆ፣ ከዚያ በኋላ በምድረበዳው ውስጥ በላማናውያን እጅ ወደ ᵐባርነት ገብ ተው ነበር፤ አዎን፣ እላችኋለሁ፣ በምርኮ ነበሩ፣ እናም በድጋሚ ጌታ በቃሉ ኃይል ᵃከባርነት አውጥቷቸዋል፤ እኛም ወደዚህ ምድር ተወስደን ነበር፣ እናም ደግሞ በዚህ ምድር ላይ የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲ ያን ማቋቋም ጀመርን።

፰ እናም አሁን እነሆ፣ ወንድሞቼ እንዲህ እላችኋለሁ፣ ከዚህ ቤተክርስቲያን የሆና ችሁ የአባቶቻችሁን በምርኮ መቆየት በሚ ገባ ታስታውሳላችሁን? አዎን፣ እናም ለእ ነርሱ ያለውንስ ምህረትና ታላቅ ፅናት በሚ ገባ ታስታውሳላችሁን? እናም ከዚህ በተ ጨማሪ፣ የእነርሱን ነፍስ ከሲያል እንዳዳነ በሚገባ ታስታውሳላችሁን?

፱ እነሆ፣ እርሱ ልባቸውን ለውጧል፣ አዎን፣ ከጥልቁ እንቅልፋቸው ቀስቅሶአ ቸዋል፣ እናም ወደ እግዚአብሔር ነቅተ ዋል። እነሆ፣ በጨለማው መካከል ነበሩ፣ ይሁን እንጂ ነፍሳቸው በዘለአለማዊው ቃል ብርሃን በርቷል፣ አዎን፣ ᵐበሞት እስራትና ᵃበሲኦል ሰንሰለት ተከበው ነበር፣ እናም ዘለአለማዊ ጥፋትም ይጠብቃቸው ነበር።

፲ እናም አሁን ወንድሞቼ እነርሱ ጠፍ ተው ነበርን? ብዬ እጠይቃችኋለሁ፣ እነሆ፣ አይደለም አልጠፉም እላችኋለሁ።

፲፡፡ እናም በድጋሚ እጠይቃለሁ፣ የሞት እስር ተሰብሯልን፣ እናም እነርሱን የከበ በው የሲኦል ሰንሰለትስ ተፈትቷል? እንዲህ እላችኋለሁ፥ አዎን፣ ተፈትቷልና፣ ነፍሳ ቸው ተስፋፋች፣ እንዲሁም በቤዛነት ፍቅር ዘምረዋል። እናም ድነዋል እላችኋለሁ።

፲፡ እናም አሁን በምን ሁኔታ ነው ᵐየዳኑት? ብዬ እጠይቃችኋለሁ፣ አዎን፣ ለመዳንስ በምንድን ነው ተስፋ ያደረጉት? ከሞት እስ ራት፣ አዎን፣ እናም ደግሞ የሲያሉ ሰን ሰለት የሚፈቱበት መንስኤ ምንድን ነው?

፲፡፡ እነሆ፣ ልነግራችሁ እችላለሁ—አባቴ አልማ ᵐበአቢናዲ አንደበት የተነገ ሩትን አላመነምን? እናም እርሱስ ቅዱስ ነቢይ አልነበረምን? የእግዚአብሔርንስ ቃላት አልተናገረምን፣ እናም አባቴ አል ማስ አላመናቸውምን?

፲፡፡ እናም በእምነቱ መሰረት በልቡ ታላቅ ᵐለውጥ ነበር። እነሆ ይህ ሁሉ እውነት ነው እላችኋለሁ።

፲፡ እናም እነሆ፣ ለአባቶቻችሁ ቃሉን ᵐሰብኳል፣ ታላቅ ለውጥም በልባቸው ውስጥ ሆነ፤ እራሳቸውንም ትሁት አደረጉ፣ ᵃእምነታቸውንም በእውነተኛውና ᵐበህያው አምላክ ላይ አደረጉ። እናም እነሆ፣ ᵐእስ ከመጨረሻው የታመኑ ነበሩ፣ ስለዚህም ድነው ነበር።

፲፡፡ እናም አሁን እነሆ፣ የቤተክርስቲ ያኗ ወንድሞቼ፣ በመንፈስ ᵐከእግዚአ ብሔር የተወለዳችሁ ናችሁን? በፊታች ሁስ ምስሉን ተቀብላችኋልን? በልባችሁስ ይህን ታላቅ ᵃለውጥ ተለማምዳችኋልን? ብዬ እጠይቃችኋለሁ።

፲፡ እናንተን ᵐበፈጠረው ስለተደረገው ቤዛነት እምነትን ተለማምዳችኋልን? ወደ

፬ ሀ ሞዛያ ፳፫፡፩–፫።
፭ ሀ ሞዛያ ፳፫፡፡ ፴፣ ፴፪–፴፬፣ ፳፰፡፡ ፳–፲፭።
ለ ሞዛያ ፳፰፡፡ ፲፯።
፯ ሀ ሞዛያ ፲፭፡፡ ፳።
ለ አልማ ፲፪፡፡ ፲፭፣ ት.እና ቃ. ፪ሠ፳፡፡ ፳፫፡፡
፲ ሀ ቅ.መ.መ. የቤዛነት ዕቅድ፣ ደህንነት።
፲፭ ሀ ሞዛያ ፲፯፡፡ ፭–፬።
፲፪ ሀ ቅ.መ.መ. መቀየር፣ የተቀየረ።
፲፡፡ ሀ ሞዛያ ፲፡፡ ፯።
ለ ቅ.መ.መ. መታመን።
ሐ ሞር. ፱፡ ፳፡፣ ት.እና ቃ. ፳፡ ፲፱።
መ ቅ.መ.መ. መፅናት።
፲፬ ሀ ሞዛያ ፳፡፯፡ ፳፬–፳፡፯፣ አልማ ፳፡፪፡ ፲፭። ቅ.መ.መ. ዳግመኛ መወለድን፣ ከእግዚአብሔር መወለድ።
ለ ሮሜ ፡፡ ፡ ፲፭–፲፯፣ ሞዛያ ፭፡ ፪፣ ሙሴ ፮፡ ፡፡፭። ቅ.መ.መ. መቀየር፣ የተቀየረ።
፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. መፍጠር፣ ፍጥረት።

ፊትስ በእምነት አይን እየተመለከታችሁ፣ ይህ ሟቹ ሰውነት የማይሞት በመሆን ፡እን ደሚነሳ፣ እናም ይህ የሚበሰብሰው ባለመ በስበስ ተነስቶ በእግዚአብሔር ፊት በሥጋ በተደረገው ስራዎች መሰረት ፡ሊፈረድበት እንደሚቆም ትመለከታላችሁን?

፲፤ እኔ እላችኋለሁ፣ በዚያን ቀን የጌታ ድምፅ ለራሳችሁ፣ እናንተ ፡የተባረካችሁ ወደ እኔ ኑ፣ እነሆ ሥራችሁ በምድር ፊት የፅድቅ ሥራ ነው እንደሚላችሁ ትገምታ ላችሁን?

፲፩ ወይንስ፣ ጌታ ሆይ፤ ስራችን በምድር ፊት ጻድቅ ስራ ነው፣ ፡ብላችሁ በዚያን ቀን ለጌታ መዋሸት እንችላለን፣ እናም እኛን ያድነናል ብላችሁ ትገምታላችሁ?

፲፪ ወይስ አለበለዚያ፣ ጥፋታችሁን ሁሉ በማስታወስ፣ አዎን፣ የክፋታችሁን ሁሉ ፍፁም ፡ትውስታ፣ እግዚአብሔርን ትእዛ ዛት ላይ ያመጻችሁትን ትውስታ እያላችሁ፣ ነፍሳችሁ በጥፋትና በፀፀት ተሞልታ በእግ ዚአብሔር ፍርድ ቤት ፊት መቅረባችሁን መገመት ይቻላችኋልን?

፲፫ እንዲህ እላችኋለሁ፣ በዚያን ቀን በን ፁህ ልባችሁና በንፁህ እጆችሁ እግዚአብ ሔርን ለመመልከት ትችላላችሁን? የእግ ዚአብሔር ፡ምስል በእናንተ ምስል ተቀ ርያ ቀና ብላችሁ መመልከት ትችላላችሁን? እላችኋለሁ።

፲፬ በዲያብሎስ ፡ተገዢ ለመሆን ራሳችሁን አሳልፋችሁ በምትሰጡበት ጊዜ ለመዳን ለማሰብ ትችላላችሁን? እላችኋለሁ።

፲፭ በዚያን ቀን መዳን እንደማትችሉ ታውቃላችሁ እላችኋለሁ፤ ማንም ሰው ፡ልብሱ ነጭ ሆኖ ካልታጠበ በቀር ፡መዳን አይችልምና፤ አዎን፣ በአባቶቻችን በተነገ ረለት፣ ህዝቡን ከኃጢአት ለማዳን በሚመ ጣው ደም ልብሱ ከሁሉም ኃጢአት ፡እስ ከሚፀዳ ድረስ ንፁህ መሆን አለበት።

፲፮ እናም አሁን፣ ወንድሞቼ እጠይቃ ችኋለሁ፣ ልብሳችሁ ፡በደምና በማንኛ ውም ዓይነት ፡ቆሻሻ ተበክሎ በእግዚአብ ሔር የፍርድ ወንበር ፊት የምትቆሙ ከሆነ ማንኛችሁም ምን ይሰማችኋል? እነሆ፣ እነ ዚህ ነገሮች በእናንተስ ላይ ምን ይመሰክ ራሉ?

፲፯ እነሆ ነፍሰ ገዳዮች፣ አዎን እናም ደግሞ በሁሉም ዓይነት ክፋት ጥፋተኛ እንደሆናችሁ ፡አይመሰክሩምን?

፲፰ እነሆ፣ ወንድሞቼ፣ እንዲህ አይ ነቱ በእግዚአብሔር መንግስት ፡ከአብር ሃም ጋር፣ ከይስሀቅ ጋር፣ እናም ከያዕቆብ ጋር፣ እናም ደግሞ ልብሳቸው የነፃና እን ከን የሌለው፣ ንፁህና ነጭ ከሆነው ከቅዱ ሳን ነቢያት ጋር ይቀመጣል ብላችሁ ትገ ምታላችሁን?

፲፱ አይደለም እላችኋለሁ፣ ፈጣሪያች ንን ከመጀመሪያ ጀምሮ ሃሰተኛ ካላደረጋ ችሁት በስተቀር፣ ወይንም እርሱ ከመጀ መሪያ ጀምሮ ሃሰተኛ ነው ብላችሁ ካል ገመታችሁ በስተቀር እንደዚህ ዓይነቱ በመንግስተ ሰማይ ቦታ ይኖረዋል ብላ ችሁ ለመገመት አትችሉም፤ ነገር ግን እነ ርሱ ፡የዲያብሎስ መንግስት ልጆች ናቸ ውና ይጣላሉ።

፲፯ እናም አሁን እነሆ፣ ወንድሞቼ እን ዲህ እላችኋለሁ፣ የልብ ፡መለወጥን የሚሰ ማችሁ ከሆነ፣ እናም የቤዛነት ፡የፍቅር ዜማ ለመዘመር ከተሰማችሁ፣ አሁንም ፡ሊሰማ ችሁ ይችላልን? በማለት እጠይቃችኋለሁ።

፲፯ ራሳችሁንስ በእግዚአብሔር ፊት

፲፭ ለ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
ሐ ቅ.መ.መ. ፍርድ፣ የመጨረሻው።
፲፯ ሀ ማቴ. ፳፭፡ ፴፭–፴፮።
፲፯ ለ ፫ ኔፊ ፲፡ ፳፡ ፳፫–፳፫።
፲፯ ሐ ሕዝ. ፳፡ ፴፫፣ ፪ ኔፊ ፱፡ ፲፡ ፣ ሞዛያ ፫፡ ፳፭፣ አልማ ፲፭፡ ፴፣ ፲፱ ሀ ፩ ዮሐ. ፫፡ ፭–፮።
፳ ሀ ሞዛያ ፪፡ ፴፪።
፳፩ ሀ ፩ ኔፊ ፲፪፡ ፣ አልማ ፲፫፡ ፣ ፲፩–፲፫፣ ፫ ኔፊ ፳፯፡ ፲፱–፳።
ለ ቅ.መ.መ. ደህንነት።
ሐ ቅ.መ.መ. ንጹህ፣ ንጹህነት።
፳፪ ሀ ኢሳ. ፶፱፡ ፫።
ለ ቅ.መ.መ. እድፍ፣ እድፍነት።
፳፫ ሀ ኢሳ. ፶፱፡ ፲፪።
፳፬ ሀ ሉቃ. ፲፫፡ ፳፰።
፳፭ ሀ ፪ ኔፊ ፱፡ ፱።
፳፯ ሀ ቅ.መ.መ. መቀየር፣ የተቀየረ።
ለ አልማ ፳፯፡ ፲፫።
ሐ ሞዛያ ፩፡ ፲፪፣ ት. እና ቃ. ፳፡ ፴፭–፴፱።

“እንከን የለሽ በማድረግ ትራመዳላችሁን? በዚህ ጊዜ ለመሞት ብትጠሩ በራሳችሁ፣ እኔ በሚገባ ፣ትሁት ነኝ? ልብሳችሁ ህዝቡን ከኃጢአቶቻቸው ሐለማዳን በሚመጣው በክርስቶስ ደም ጠርቷልን፣ እናም ነጥቷል ለማለት ትችላላችሁን?

፳፯ እነሆ፣ “ከኩራታችሁስ ተገፍፋችኋልን? ካልሆናችሁ እግዚአብሔርን ለመገናኘት ዝግጁ አይደላችሁም እላችኋለሁ። እነሆ በፍጥነት መዘጋጀት አለባችሁ፤ መንግስተ ሰማይ ቀርባለችና፣ እናም እንደዚህ ዓይነቱ ዘለአለማዊ ህይወት አይኖረውም።

፳፰ እነሆ፣ እላለሁ፣ ከእናንተ መካከል “ከምቀኝነት ያልተገፈፈ አንድ እንኳን አለን? እንደዚህ ዓይነቱ አልተዘጋጀም እላችኋለሁ፤ እናም ጊዜው ቀርቧልና በፍጥነት እንዲዘጋጅ እፈልገዋለሁ፣ እናም ጊዜው መቼ እንደሚመጣ አያውቅም፤ እንደዚህ ዓይነቱ እንከን የሌለው ሆኖ አልተገኘምና።

፳ እናም በድጋሚ እላችኋለሁ፣ በወንድሙ ላይ ከእናንተ መካከል “የሚሳለቅ፣ ወይም ስደትን የሚያበዛ አለን?

፳፩ ለእንደዚህ ዓይነቱ አልተዘጋጀምና ወዮለት፣ እናም ጊዜው ቀርቧልና ንስሀ መግባት አለበት፣ አለበለዚያም መዳን አይችልም!

፳፪ አዎን፣ እናንተ “ክፋትን ለምትሰሩ ሁሉ ወዮላችሁ፣ ንስሀ ግቡ፣ ንስሀ ግቡ፣ ጌታ እግዚአብሔር ተናግሮታልና!

፳፫ እነሆ፣ ለሰው “ሁሉ ግብዣን ልኳል፣ ^የምህረት ክንድ ወደእነርሱ ተዘርግቷልና፣ እናም እንዲህ ይላል፥ ንስሀ ግቡ፣ እናም እኔ እቀበላችኋለሁ።

፳፬ አዎን፣ እንዲህም ይላል፥ ወደ እኔ “ኑ፣ እናም ከህይወት ዛፍም ^ፍሬ ትካፈላላችሁ፤ አዎን የህይወትን ሐዳቦና ውኃ ”በነፃ ትመገባላችሁ እናም ትጠጣላችሁ፤

፳፭ አዎን፣ ወደ እኔ ኑና፣ የፅድቅንም ስራ አቅርቡ፣ እናም አትቆረጡም በእሳት ውስጥም አትጣሉም—

፳፮ እነሆ፣ “መልካም ያልሆነውን ፍሬ የሚያመጣ፣ ወይም የፅድቅን ስራ የማይሰራ እንዲያዝንና እንዲያለቅስ የሚሆንበት ጊዜው ቀርቧልና።

፳፯ እናንተ የተንኮል ሰራተኞች ሆይ፤ በዓለም “ከንቱ ነገሮች በኩራት የተሞላችሁ፤ የፅድቅን መንገድ ማወቃችሁን የምትናገሩ ነገር ግን እረኛ እንደሌለው ^በግ ሐበተሳሳተው የምትጓዙ፤ ሆኖም እረኛው ”ጠርቷችኋል እናም አሁንም እናንተን ይጣራል፣ ነገር ግን እናንተ ድምፁን “አትሰሙም!

፳፰ እነሆ፣ መልካሙ “እረኛ እናንተን ይጣራል እላችኋለሁ፤ አዎን፣ እናም በክርስቶስ ስም በሆነው በስሙ ይጠራችኋል፤ እናም በምትጠሩበት ^ስም የመልካሙን እረኛ ድምፅ ሐየማትሰሙ ከሆነ፣ እነሆ፣ እናንተ ”የመልካሙ እረኛ በግ አይደላችሁም!

፳፱ እናም አሁን የመልካሙ እረኛ በግ ካልሆናችሁ፣ ከየትኛው “በረት ናችሁ? እነሆ፣ ^ዲያብሎስ እረኛችሁ ነው እላችኋለሁ፣ እናም እናንተም ከእርሱ በረት ናችሁ፣ እናም አሁን ይህንን ማን ሊክደው ይቻለ

፳፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. ማፅደቅ፣ ከበደል ነጻ መሆን።
ለ ቅ.መ.መ. ትሁት፣ ትሕትና።
ሐ ቅ.መ.መ. ቤዛ፣ ማዳን፣ ቤዛነት።
፳፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. ኩራት።
፳፱ *ሀ* ቅ.መ.መ. ቅናት።
፴ *ሀ* ቅ.መ.መ. ክፉ መናገር።
፴፪ *ሀ* መዝ. ፭፡ ፭።
፴፫ *ሀ* አልማ ፲፱፡ ፴፯፤
ቮ ኔፊ ፲፯፡ ፳፭።
ለ ያዕቆ. ፯፡ ፭፤
ቮ ኔፊ ፱፡ ፲፱።
፴፬ *ሀ* ፪ ኔፊ ፳፯፡ ፳፬–፳፯፤
ቮ ኔፊ ፱፡ ፲፫–፲፬።
ለ ፩ ኔፊ ፳፡ ፲፭፤ ፲፭፡ ፴፯።
ሐ ቅ.መ.መ. የህይወት እንጀራ።
መ ፪ ኔፊ ፱፡ ፣–፴፩፤
አልማ ፵፪፡ ፳፯።
፴፯ *ሀ* ማቴ. ፫፡ ፣፤ ፯፡ ፲፭–፳፤
ቮ ኔፊ ፲፬፡ ፲፱፤
ት. እና ቃ. ፣፲፯፡ ፯።
፴፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. ከንቱ፣ ከንቱነት።
ለ ማቴ. ፱፡ ፴፯።
ሐ ፪ ኔፊ ፲፪፡ ፳፤ ፳፯፡ ፲፲፤
ሞዛያ ፲፡ ፯።
መ ምሳ. ፩፡ ፳፭–፳፯፤
ኢሳ. ፳፭፡ ፲፪።
ቮ ኔፊ ፱፡ ፲ቮ–፲፩።
ለ ፩ ኔፊ ፳፡ ፲፭፤ ፲፭፡ ፴፯።
ሐ ቅ.መ.መ. የህይወት እንጀራ።
መ ፪ ኔፊ ፱፡ ፣–፴፩፤
አልማ ፵፪፡ ፳፯።
፴፯ *ሀ* ማቴ. ፫፡ ፣፤ ፯፡ ፲፭–፳፤
ቮ ኔፊ ፲፡ ፲፱፤
ት. እና ቃ. ፣፲፯፡ ፯።
፴፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. ከንቱ፣ ከንቱነት።
ለ ማቴ. ፱፡ ፴፯።
ሐ ፪ ኔፊ ፲፪፡ ፳፤ ፳፯፡ ፲፲፤
ሞዛያ ፲፡ ፯።
መ ምሳ. ፩፡ ፳፭–፳፯፤
ኢሳ. ፳፭፡ ፲፪።
ሠ ኤር. ፳፯፡ ፱–፭፤
አልማ ፲፡ ፯።
፴፰ *ሀ* ቅ.መ.መ. መልካሙ እረኛ።
ለ ሞዛያ ፭፡ ፣፤
አልማ ፴፡ ፴፣።
ሐ ዘሌዋ. ፳፯፡ ፲፡–፭፤
ት. እና ቃ. ፲፩፡ ፯።
መ ቮ ኔፊ ፲፭፡ ፳፡ ፲፣፡ ፴፩።
፴፱ *ሀ* ማቴ. ፯፡ ፳፡፤
ሉቃ. ፲፯፡ ፲ቮ።
ለ ሞዛያ ፭፡ ፣።
ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።

ዋል? እነሆ ይህን የካደ ሐውሽታም እንዲ ሁም መየዲያብሎስ ልጅ ነው እላችኋለሁ።

፵ ማንኛውም ᵇመልካም የሆነ የሚመጣው ከእግዚአብሔር ነው፣ ማንኛውም ክፉ የሆ ነው የሚመጣው ከዲያብሎስ ነው እላች ኋለሁ።

፵፩ ስለዚህ፣ ᵇመልካም ስራዎችን የሚያ መጣ የመልካሙን እረኛ ድምፅ ይሰማል፣ እና እርሱንም ይከተለዋል፤ ነገር ግን ክፉ ስራዎች የሚያመጣ፣ ያም ᵃየዲያብሎስ ልጅ ይሆናል፣ ድምፁን ይሰማዋል፣ እናም ይከተለዋልና።

፵፪ እናም ይህን ያደረገ ᵇደምዎዙን ከእ ርሱ መቀበል ይገባዋል፤ ስለዚህ፣ የፅድቅ ስራዎችን በተመለከተ፣ ለመልካም ስራ ዎች ሁሉ ሙት በመሆን፣ ᵃለደሞዙ የሚ ያገኘው ሐሞት ነው።

፵፫ እናም አሁን፣ ወንድሞቼ፣ እንድ ታዳምጡኝ እፈልጋለሁ፣ በነፍሴ ሀይል እናገራለሁና፤ እነሆ ልትሳሳቱ በማትች ሉበት ሁኔታ በግልፅ ተናግሬአችኋለሁና፣ ወይም በእግዚአብሔር ትዕዛዛት መሰረት ተናግሬአችኋለሁ።

፵፬ እኔም ክርስቶስ ኢየሱስ በሆነው፣ በእ ግዚአብሔር ᵇቅዱሱ ስርዓት መሰረት በዚህ ሁኔታ እንድናገር ተጠርቻለሁ፤ አዎን፣ የሚመጡትን ነገሮች በሚመለከት በአባ ቶቻችን የተነገሩትን ነገሮች ለዚህ ህዝብ ቆሜ እንድመሰክር ታዝዜአለሁ።

፵፭ እናም ይህ ብቻም አይደለም። እነዚ ህን ነገሮች እኔ ራሴ ᵇእንደማውቃቸው አት ገምቱምን? እነሆ፣ እነዚህ የምናገራቸው ነገሮች እውነት መሆናቸውን እንደማውቅ እመሰክርላችኋለሁ። እናም እርግጠኝነታ ቸውን እንዴት እንዳወቅሁ ትገምታላችሁ?

፵፮ እነሆ፣ እነዚህ ᵇእንዲታወቁኝ የሆ ኑት በእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ ነው። እነሆ፣ እነዚህን ነገሮች ለራሴ ለማወቅ ለብዙ ቀናት ᵃፆሜአለሁ እንዲሁም ፀል ያለሁ። እናም አሁን እውነት መሆናቸውን ለራሴ አውቄአለሁ፤ ጌታ እግዚአብሔር በቅዱስ መንፈሱ እንዲገለፅልኝ አድርጓ ልና፤ እናም ይህ በእኔ ውስጥ ያለው ᵃየራ ዕይ መንፈስ ነው።

፵፯ እናም ከዚህ በተጨማሪ፣ የእግዚአ ብሔር መንፈስ መገለጫ በሆነው፣ በእኔ ውስጥ ባለው የትንቢት መንፈስም መሠረ ትም፣ በአባቶቻችን የተነገሩት ቃላት እው ነት መሆናቸው እንደተገለፀልኝ እነግራ ችኋለሁ።

፵፰ የሚመጣውን በተመለከተ ማንኛውም ለእናንተ የምናገረው እውነት እንደሆነ እኔ ራሴ እንደማውቀው እነግራችኋለሁ፤ እናም እላችኋለሁ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ አዎን፣ በጸጋና፣ በመሀሪነት፣ እንዲሁም በእው ነት የተሞላው የአብ አንድያ ልጅ፣ እንደ ሚመጣ አውቃለሁ። እናም እነሆ የዓለምን ኃጢያት፣ አዎን፣ በፅናት በስሙ የሚያምኑ ሰዎች ሁሉ ኃጢያትን ለመውሰድ የሚመ ጣው እርሱ ነው።

፵፱ እናም አሁን እላችኋለሁ ይህ እኔ፣ አዎን፣ ለውድ ወንድሞቼ እንድሰብክ፤ አዎን፣ እናም በምድሪቱ ላይ ለሚኖሩ ሁሉ፣ አዎን፣ ለወጣትና ለሽማግሌዎች፣ ለታሰሩትና ነፃ ለሆኑት ሁሉ እንድሰብክ፤ አዎን፣ እላችኋለሁ፣ ለሽማግሌዎችና፣ ደግሞ መካከለኛ ዕድሜ ላላቸው፣ እናም በማደግ ላይ ላለው ትውልድ፤ አዎን፣ ንስሀ እንዲገቡና ᵇዳግም እንዲወለዱ ወደ እነርሱ እንድጮህ ᵃየተጠራሁበት ሥርዓት ነው።

፴፱ *ሐ* ፩ ዮሐ. ፪፡ ፳፪።
መ ፪ ኔፊ ፱፡ ፱።
፵ *ሀ* ኦምኒ ፩፡ ፳፭፤
ኤተር ፭፡ ፲፪፤
ሞሮኒ ፯፡ ፲፪፣ ፲፭–፲፯።
፵፩ *ሀ* ፫ ኔፊ ፲፡ ፲፯–፳።
ቅ.መ.መ. ስራዎች።
ለ ሞዛያ ፲፯፡ ፫–፭፤
አልማ ፲፩፡ ፳፫።
፵፪ *ሀ* አልማ ፫፡ ፳፯–፳፯፤
ት. እና ቃ. ፳፱፡ ፵፭።
ለ ሮሜ ፮፡ ፳፫።
ሐ ሔለ. ፲፬፡ ፲፯–፲፰።
ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ሞት።
፵፫ *ሀ* አልማ ፲፫፡ ፮።
፵፭ *ሀ* ቅ.መ.መ. ምስክርነት።
፵፮ *ሀ* ፩ ቆሮ. ፪፡ ፱–፲፯።
ለ ቅ.መ.መ. ጸም፣ መጸም።
ሐ ቅ.መ.መ. ራዕይ።
፵፱ *ሀ* ቅ.መ.መ. ዳግመኛ
መወለድን፣ ከእግዚአብሔር
መወለድ።
ለ ቅ.መ.መ. ክህነት፣
ጥሪ፣ በእግዚአብሔር
መጠራት፣ የተጠራበት።

፱ አዎን፣ መንፈስ እንዲህ ይላል፡ በአለም ዳርቻዎች ያላችሁ ሁሉ ንስሀ ግቡ፣ መንግስተ ሰማያት ቀርባለችና፣ አዎን፣ የእግዚአብሔር ልጅ በኃይሉ፣ [ሀ]በግርማ ሞገሱ፣ በአገዛዙና በስልጣኑ፣ በክብሩ ይመጣል። አዎን፣ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ፣ መንፈስ እንዲህ ይላል እላችኋለሁ፤ [ለ]የምድር ንጉስ ሁሉ ክብር ተመልከቱ፤ እናም ደግሞ የሰማይ ንጉስ በቅርቡ በሰው ልጆች ሁሉ መካከል ያበራል።

፲፩ እናም ደግሞ መንፈስ እንዲህ አለኝ፣ አዎን፣ በከፍተኛ ድምፅ ወደ እኔ እንዲህ በማለት ጮኸ፤ ሂድና ለህዝቡ እንዲህ በል—ንስሀ ግቡ፣ ንስሀ ካልገባችሁ በስተቀር በምንም ዓይነት መንገድ [ሀ]መንግስተ ሰማያትን አትወርሱም።

፲፪ እናም በድጋሚ እንዲህ እላችኋለሁ፣ መንፈስ እንዲህ ይላል፡ እነሆ፣ [ሀ]ምሳር በዛፉ ስር ተቀምጧል፤ እንግዲህ መልካም ፍሬ የማይሰጥ ዛፍ ሁሉ [ለ]ይቆረጣል ወደ እሳትም፣ አዎን፣ ወደማይቆም እሳት፣ ወደማይጠፋ እሳት ይጣላል። እነሆ፣ እናም አስታውሱ፣ ይህን ቅዱሱ ተናግሮታል።

፲፫ እናም አሁን የተወደዳችሁ ወንድሞቼ፣ እንዲህ እላችኋለሁ፣ ይህንን አባባል ልትቃወሙት ትችላላችሁን፤ አዎን፣ እነዚህ ነገሮችን ችላ ልትሉአቸው ትችላላችሁን፣ እናም ቅዱሱንስ በእግራችሁ ስር [ሀ]ትረግጡታላችሁን፤ አዎን፣ በልባችሁ [ለ]ኩራትስ ለመወጠር ይቻላችኋልን፤ አዎን፣ [ሐ]ውድ የሆኑ ልብሶችን በመልበስ እናም ልባችሁን በከንቱ ምድራዊ ነገሮች እንዲሁም [መ]በሀብት ላይ ማድረጋችሁን አሁንም ትቀጥላላችሁን?

፲፬ አዎን፣ እናንተን ከሌሎች የተሻላችሁ አድርጋችሁ መገመትን ትቀጥላላችሁን? አዎን፣ በእግዚአብሔር ቅዱሱ ስርዓት የሚራመዱትንና እራሳቸውን ትሁት ያደረጉትን ወንድሞቻችሁን ማሳደድ ትቀጥላላችሁ? በዚህም ወደዚህች ቤተክርስቲያን መጥተዋል፣ በቅዱሱ መንፈስ [ሀ]ተቀድሰዋል፣ እናም ለንስሀ የሚያበቁአቸውን ስራዎቻቸውንም አምጥተዋል—

፲፭ አዎን [ሀ]በድሆች ላይና በተቸገሩ ላይ ትከሻችሁን ማዞር፣ እንዲሁም ያሉአችሁን ሳታካፍሉ ትቀጥላላችሁን?

፲፮ እናም በመጨረሻ፣ በክፋታችሁ የምትቀጥሉ ሁሉ፣ በፍጥነት ንስሀ ካልገቡ በስተቀር ተቆርጠው ወደ እሳቱ የሚጣሉት እነርሱ እንደሆኑ እነግራችኋለሁ።

፲፯ እናም አሁን [ሀ]የመልካሙን እረኛ ድምፅ ለመከተል የምትፈልጉ ሁሉ፣ ከክፉዎች ውጡና [ለ]ተለዩ፣ እንዲሁም እርኩስ ነገሮቻቸውን አትንኩ እላችኋለሁ፤ እናም እነሆ፣ የኃጢአተኞች ስም ከህዝቤም ጋር አይቀላቀልም፣ የተባለው የእግዚአብሔር ቃል ይፈፀም ዘንድ ስማቸው [ሐ]ይሰረዛል፣ የክፉዎች ስም ከፃድቃኖች ጋርም አይቆጠርም።

፲፰ የፃድቃኖች ስም [ሀ]በህይወት መፅሐፍ ይፃፋል፤ እናም ለእነርሱ በቀኝ እጄ ያለውን ውርስ እሰጣቸዋለሁ። እናም አሁን ወንድሞቼ ከዚህ ተቃራኒ የሆነን ምን ትናገራላችሁ? እላችኋለሁ፣ ከዚህ ተቃራኒ የምትሉ

፱ *ሀ* ቅ.መ.መ. ክብር፤ የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
ለ መዝ. ፳፬፡ ማቴ. ፪፡፪፣ ሉቃ. ፳፣፡፣ ፪ ኔፊ ፲፡፲፣ ት. እና ቃ. ፴፰፡፳፩–፳፪፣ ፲፫፡፳–፳፪፣ ሙሴ ፯፡፶፣ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ፤ የእግዚአብሔር መንግስት ወይም መንግስተ ሰማያት።

፱፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. ሰማይ።
፱፪ *ሀ* ሉቃ. ፫፡፱፣ ት. እና ቃ. ፶፯፡፯።
ለ ያዕቆ. ፭፡፴፯፣ ፯፡፯፣ ፫ ኔፊ ፳፯፡፲፩–፲፪።
፱፫ *ሀ* ፩ ኔፊ ፲፱፡፯።
ለ ቅ.መ.መ. ኩራት።
ሐ ፪ ኔፊ ፳፰፡፲፩–፲፡፣ ሞር. ፰፡፴፯–፴፱።
መ መዝ. ፰፪፡፲፣ ት. እና ቃ. ፶፯፡፲፯–፲፰።
፱፬ *ሀ* ቅ.መ.መ. ቅድስና።
፱፭ *ሀ* መዝ. ፲፱፡፲፭–፲፯፣ ያዕቆ. ፪፡፲፣ ሔለ. ፯፡፴፱–፴፡ ።
፱፮ *ሀ* ቅ.መ.መ. መልካሙ እረኛ።
ለ ዕዝ. ፯፡፳፭፣ ፱፡፭፣ ነህ. ፱፡፪፣ ፪ ተሰ. ፫፡፯፣ ት. እና ቃ. ፲፴፫፡፭፣ ፲፩።
ሐ ዘዳግ. ፳፱፡፳፣ ሞሮኒ ፯፡፯፣ ት. እና ቃ. ፳፡፰።
፱፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. የሕይወት መፅሐፍ።

ከሆነ፣ ይህ ምንም አይደለም፣ የእግዚአብሔር ቃል ይፈጸማልና።

፶፱ በእናንተ መካከል የትኛው እረኛ ነው ብዙ በጎች እያሉት፣ ተኩላዎችስ ገብተው መንጋዎቹን እንዳይበሉበት የማይጠብቃቸው? እናም እነሆ፣ ተኩላው ሲገባበት እርሱ አያባርርምን? አዎን፣ እናም የሚቻለው ከሆነ እርሱንም ያጠፋዋል።

፷ እናም አሁን መልካሙ እረኛ ይጠራችኋል እላችኋለሁ፤ እናም ቃሉን የምታዳምጡ ከሆነ ወደ በረቱ ያመጣችኋል፤ እናንተም የእርሱ በጎች ናችሁ፤ እንዳትጠፉ ደም የተጠማውን ተኩላ በመካከላችሁ እንዲገባ እንዳትፈቅዱም ያዛችኋል።

፷፩ እናም አሁን እኔ፣ አልማ፣ እኔ የተናገርኳችሁንም ቃላት እንድታደርጉ፣ እኔን ባዘዘኝ [ሀ]በእርሱ ቋንቋ አዛችኋለሁ።

፷፪ ከቤተክርስቲያኗ ለሆናችሁ በትዕዛዝ መልክ እናገራለሁ፤ እናም ከቤተክርስቲያኗ ላልሆኑት በግብዣ መልክ እንዲህ በማለት እናገራለሁ፥ [ሀ]የህይወት ዛፍ ፍሬን ደግሞ ትካፈሉ ዘንድ ኑ እናም ለንስሀ ተጠመቁ።

ምዕራፍ ፬

በዛራሄምላ ያለው ቤተክርስቲያን ከኃጢያት ጠርቷል እናም ተደራጅቷል—አልማ ለመስበክ ወደ ጌዴዎን ሄደ። ፹፫ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም አሁን እንዲህ ሆነ አልማ በዛራሔምላ ከተማ ለተቋቋመው ቤተክርስቲያን ሰዎች ንግግሩን ከጨረሰ በኋላ፣ በእግዚአብሔር ስርዓት መሰረት ቤተክርስቲያኗን እንዲመሩና [ሀ]እንዲቆጣጠሩ [ለ]እጁን በመጫን ካህናትን እና [ሐ]ሽማግሌዎችን [መ]ሾመ።

፪ እናም እንዲህ ሆነ ከቤተክርስቲያኗ ያልሆኑ ለኃጢአታቸው ንስሐ የገቡት ወደ ንስሐ [ሀ]ተጠምቀው እናም በቤተክርስቲያኗ ተቀባይነትን አግኝተው ነበር።

፫ እናም ደግሞ እንዲህ ሆነ ከቤተክርስቲያኗ የሆኑ ለኃጢአታቸው [ሀ]ንስሐ ያልገቡ እናም በእግዚአብሔር ፊት እራሳቸውን ዝቅ የማያደርጉ ሁሉ—ማለትም በልባቸው [ለ]ኩራት የተወጠሩ—እንደነዚህ ዓይነቶቹ ተቀባይነትን አላገኙም ነበር፣ እናም ስማቸው [ሐ]ተሰርዘዋል፣ ስማቸው ከፃድቃኖች ጋር አልተቀጠረም ነበር።

፬ እና እንደዚህም በዛራሔምላ ከተማ የቤተክርስቲያኗን ስርዓት መመስረት ጀመሩ።

፭ አሁን የእግዚአብሔር ቃል ለሁሉም በነፃ እንደተሰጠ እንድትረዱ እፈልጋለሁ፣ ማንም እራሱን በአንድ ላይ በመሰብሰብ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት ልዩ መብቱን የሚከለክለው የለም።

፮ ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ልጆች እራሳቸውን በአንድ ላይ ሁልጊዜ እንዲሰበሰቡ፣ እናም በአንድ ላይ በመሆን እግዚአብሔርን ለማያውቁት ነፍሳት ደህንነት [ሀ]እንዲፆሙና እንዲፀልዩ ታዘዋል።

፯ እናም አሁን እንዲህ ሆነ አልማ እነዚህን ህጎች ባዘጋጀ ጊዜ ከእነርሱ፣ አዎን፣ በዛራሔምላ ከተማ ከሚገኘው ቤተክርስቲያን፣ ተለይቶ ሄደ፣ እናም [ሀ]በጌዴዎን ሸለቆ፣ ከሲዶም ወንዝ በስተምስራቅ በኩል ጌዴዎን ተብላ ወደ ምትጠራውና በዚያም ወደታነፀች ከተማ፣ ጌዴዎን ተብሎ ወደ ሚጠራው ሸለቆ ሄደ፣ ስፍራውም ኔሆር በተባለው ሰው እጅ [ለ]በተገደለው ስም የሚጠራ ነበር።

፰ እናም አልማ ሄደና፣ በአባቶቹ በተነገረው በቃሉ እውነታ ራዕይ መሰረትና፣ በውስጡ ባለው የትንቢት መንፈስ፣ የእግዚአብሔር ልጅ በሆነው፣ ህዝቡን ከኃጢ

፷፩ ሀ አልማ ፫፥ ፴፰።
፷፪ ሀ ፩ ኔፊ ፰፥ ፲፤ ፲፩፥ ፳፩–፳፫።
፬ ፩ ሀ ት. እና ቃ. ፶፪፥ ፴፱።
ለ ቅ.መ.መ. እጅን መጫን።
ሐ ቅ.መ.መ. ሽማግሌ።
መ ቅ.መ.መ. መሾም፣ ሹመት።
፪ ሀ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣ መጥመቅ።
፫ ሀ ሞዛያ ፳፮፥ ፮።
ለ ቅ.መ.መ. ኩራት።
ሐ ዘፀአ. ፴፪፥ ፴፫፤ ሞዛያ ፳፮፥ ፴፮፤ አልማ ፩፥ ፳፬፤ ፫፥ ፶፯–፶፰።
ቅ.መ.መ. ውግዘት።
፮ ሀ ቅ.መ.መ. ጾም፣ መጾም።
፯ ሀ አልማ ፪፥ ፳።
ለ አልማ ፩፥ ፱።

ያት ለማዳን በሚመጣውና ᵐበኢየሱስ ክር ስቶስ ምስክርነት መሰረትና፣ በተጠራበ ትም ቅዱሱ ስርዓት፣ በጌዴዎን ሸለቆ ለተ ቋቋመችው ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔ ርን ቃል ማወጅ ጀመረ። እናም እንዲሁ ተፅፏል። አሜን።

እንደራሱ መዝገብ መሰረት፣ በጌዴዎን ከተማ አልማ ለህዝቡ የተናገረው ቃላት።

ምዕራፍ ፯ አጠቃሎ የያዘ።

ምዕራፍ ፯

ክርስቶስ ከማርያም ይወለዳል—የምትን አስራት ይፈታል፣ እናም የሕዝቡን ኃጢ ያት ይሸከማል—ንስሐ የሚገቡ፣ የሚጠ መቁ፣ እናም ትዕዛዛቱን የሚጠብቁ ዘለ አለማዊ ህይወት ይኖራቸዋል—ርኩ ሰት የእግዚአብሔርን መንግስት ለመ ውረስ አይቻለውም—ትህትና፣ እም ነት፣ ተስፋና ልግስና አስፈላጊ ናቸው። በ፲፰ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እነሆ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ፣ ወደ እናንተ እንድመጣ እስከተፈቀደልኝ ድረስ፣ ስለሆነም በራሴ አባባል ለመናገር እሞክራለሁ፤ አዎን፣ በራሴ አንደበት፣ በራሴ ቃል ᵐለእናንተ ለመናገር የመጀመ ሪያዬ በመሆኑ፣ ᵃበፍርድ ወንበር ብቻ እን ድሆን በመደረጌ፣ ብዙ ስራ ስላለብኝ ወደ እናንተ ለመምጣት አልቻልኩም ነበር።

፪ እናም አሁን የፍርድ ወንበር በእኔ ቦታ ሌላው እንዲገዛ ᵐባይሰጥ ኖሮ፣ አሁን በዚህ ጊዜ ለመምጣት አይቻለኝም ነበር፤ እናም ጌታ በታላቅ ምህረቱ ወደ እናንተ እንድ መጣ ፈቅዷል።

፫ እናም እነሆ፣ እናንተ በእግዚአብሔር ፊት ራሳችሁን ዝቅ አድርጋችሁ እንዳገኛ ችሁ፣ ፀጋውን ያለማቋረጥ ለምናችኋል፣ እናም በፊቱ እንከን የሌላችሁ ሆናችሁ እንዳገኛችሁ፣ ወንድሞቻችን በዛራሔምላ እንደነበሩበት በመጥፎ ሁኔታ ሳትሆኑ እን ዳገኛችሁ በታላቅ ተስፋና ፍላጎት መጥ ቻለሁ።

፬ ነገር ግን እንድረዳ ያደረገኝ የእግዚአብ ሔር ስም የተባረከ ይሁን፤ አዎን፣ እነርሱ በድጋሚ በፅድቁ ሲቋቋሙ የማወቅ እጅግ ታላቅ ደስታን ሰጥቶኛል።

፭ እናም ውስጤ ባለው የእግዚአብ ሔር መንፈስ መሰረት፣ በእናንተም ላይ ደግሞ ደስታ ይኖረኛል ብዬ አምናለሁ፤ ይሁን እንጂ እኔ በእናንተ ላይ ያለኝ ደስታ በዛራሔምላ በነበሩ ወንድሞች በነበረኝ ስቃይና ሀዘን ምክንያት እንዲመጣ አልፈ ልግም፤ እነሆ፣ በእነርሱ ላይ የነበረኝ ደስ ታዬ የመጣው በብዙ መከራና ስቃይ ከተ ገፋሁ በኋላ ነበር።

፮ ነገር ግን እነሆ፣ እናንተ ግን እንደ ወን ድሞቻችሁ ባለማመን ሁኔታ ውስጥ እን ዳልሆናችሁ አምናለሁ፤ በልባችሁ ኩራት እንደማትወጠሩም አምናለሁ፤ አዎን፣ ልባችሁን በሀብት ላይ እናም በዓለም ከንቱ ነገሮች ላይ እንደማታደርጉት አምናለሁ፤ አዎን፣ ᵐጣዖትን እንደማታመልኩ፣ ነገር ግን እውነተኛውንና ᵃሕያው እግዚአብሔ ርን እንደምታመልኩ፣ እናም የሚመጣውን የኃጢአታችሁ ስርየትን ዘለአለማዊ በሆነው እምነት እንደምትጠብቁ አምናለሁ።

፯ እነሆም፣ ብዙ ነገር ይመጣል እላችኋ ለሁ፤ እናም እነሆ፣ ከሁሉም የበለጠ አንድ ነገር አለ—እነሆም አዳኙ የሚመጣበትና ከህዝቡ ጋር የሚኖርበት ᵐጊዜ ሩቅ አይደ ለም።

፰ እነሆ በስጋ ሰውነቱ በሚኖርበት ጊዜ በመካከላችን ይገኛል አልልም፤ እነሆም መንፈስም ሁኔታው ይህ ነው አላለኝም። አሁን ይህንን በተመለከተ አላውቅም፤ ነገር

፰ ሀ ራዕ. ፲፱፡፲። ፯ ፩ ሀ አልማ ፬፡፲፱። ለ ሞዛያ ፳፱፡፵፪። ፪ ሀ አልማ ፬፡፲፮–፲፰። ፯ ሀ ፪ ኔፊ ፱፡፴፯፤ ሔለ. ፯፡፴፩። ለ ዳን. ፯፡፳፯። ፯ ሀ አልማ ፱፡፳፯።

ግን እስከዚህ ድረስ አውቃለሁ፣ ጌታ እግ
ዚአብሔር ቃሉ መሰረት ሁሉንም ነገሮች
ለማድረግ ሀይል እንዳለው አውቃለሁ።

፱ ነገር ግን እነሆ፣ መንፈስ እንዲህ በማ
ለት ይህን ያህል ተናግሮኛል፤ ወደ ህዝቡ
እንዲህ ስትል ጨህ—[ሀ]ንስሐ ግቡ፣ እናም
የጌታን መንገድ አዘጋጁና፣ ቀጭን በሆኑት
ጎዳናዎች ተራመዱ፤ እነሆም፣ መንግስተ
ሰማያት ቀርባለችና እናም የእግዚአብሔር
ልጅ [ለ]በምድር ፊት ይመጣል።

፲ እናም እነሆ፣ እርሱም [ሐ]ከማርያም [ለ]በቅ
ድመ አባቶቻችን ምድር በሆነችው በኢየ
ሩሳሌም [መ]ይወለዳል፣ እርሷም [ሠ]ድንግል፣
በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በመሸፈን፣ የተከበ
ረች እንዲሁም የተመረጠች ዕቃ ሆና [ሠ]በመ
ፀነስ ወንድ ልጅ፣ አዎን እንዲሁም የእግ
ዚአብሔር ልጅ፣ ትወልዳለች።

፲፩ እናም በመከራና በሁሉም ዓይነት
ህመምና ፈተናዎች [ሀ]በመሰቃየት ይሄዳል፤
የህዝቡን ህመምና በሽታ በራሱ ላይ ይወ
ስዳል የሚለውን ቃል ይፈፀም ዘንድ ይህ
ይሆናል።

፲፪ እናም ህዝቡን ያሰረውን የሞት እስር
ይፈታ ዘንድ [ሀ]ሞትን በራሱ ላይ ይወ
ስዳል፣ እናም በስጋ አንጀቱ በምህረት
ይሞላ ዘንድ፣ በስጋ ህዝቡን ከድካሙ እን
ዴት [ለ]እንደሚረዳ ያውቅ ዘንድ ድካማች
ውን በራሱ ላይ ያደርጋል።

፲፫ እንግዲህ መንፈስ ሁሉን ነገር [ሀ]ያው
ቃል፤ ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ልጅ
ሰዎችን በማዳን ኃይሉ መተላለፋቸውን
ይሰርይላቸው ዘንድ የህዝቡንም ኃጢያት
[ለ]በራሱ ላይ ያደርግ ዘንድ በስጋው ይሰቃ
ያል፤ እናም አሁን እነሆ በእኔ ያለው ምስ
ክርነት ይህ ነው።

፲፬ እንግዲህ እናንተ ንስሐ መግባትና፣
[ሀ]በድጋሚ መወለድ አለባችሁ እላለሁ፤
መንፈስም በድጋሚ ካልተወለዳችሁ መን
ግስተ ሰማያትን መውረስ አትችሉም ይላ
ልና፤ ስለዚህ ከኃጢአታችሁ ትነፁ ዘንድ
የዓለምን ኃጢያት በወሰደው፣ ለማዳንና
መጥፎ ከሆኑት ሁሉ ለማፅዳት ኃያል በሆ
ነው በእግዚአብሔር በግ እምነት ይኖራችሁ
ዘንድ ኑ እናም ለንስሀ ተጠመቁ።

፲፭ አዎን ኑና አትፍሩ፣ እናም በቀላሉ
[ሀ]የሚጎዳችሁን ማንኛውንም ኃጢያት ወደ
ጥፋት እንድታመሩ የሚያደርጋችሁን አስ
ወግዱ እላችኋለሁ፤ አዎን፣ ኑና ወደ ፊት
ቀጥሉ እናም ለኃጢአታችሁ ንሰሃ ለመግ
ባትና፣ ትእዛዛቱን ለመጠበቅ ፈቃደኛ እን
ደሆናችሁ፣ እናም በዚህ ቀንም ይህን ወደ
ጥምቀት ውኃ በመሄድ ለእግዚአብሔር
በምስክር አሳዩት።

፲፮ እናም ማንም ይህንን ቢያደርግና፣
ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የእግዚአብሔርን ትዕዛ
ዛት ቢጠብቅ ይህንኑ እንዳልኩት ያስታው
ሳል፤ አዎን፣ በውስጤ ያለው ቅዱስ መን
ፈስ በመሰከረልኝ መሰረት ዘለአለማዊ ህይ
ወት እንደሚኖረው የተናገርኩትን ያስታ
ውሳል።

፲፯ እናም አሁን የተወደዳችሁ ወንድ
ሞቼ፣ እነዚህን ነገሮች ታምናላችሁን?
እነሆ፣ እላችኋለሁ፣ አዎን እነርሱን ማመ
ናችሁን አውቃለሁ፤ እናም እነርሱን ማመ
ናችሁን የማውቀው በውስጤ ባለው መን
ፈስ መገለጥ ነው። እናም አሁን ይህን በተ

፱ ሀ ማቴ. ፫፡ ፪–፬፤
አልማ ፱፡ ፳፯።
ለ ሞዛያ ፫፡ ፭፤ ፯፡ ፳፯፤
፲፭፡ ፩–፪።
፲ ሀ ሞዛያ ፫፡ ፳።
ቅ.መ.መ. ማርያም፣
የኢየሱስ እናት።
ለ ፩ ዜና ፱፡ ፫፤
፪ ዜና ፲፭፡ ፱፤
፩ ኔፊ ፩፡ ፡፡
፫ ኔፊ ፳፡ ፳፱።
ሐ ኢሳ. ፯፡ ፲፡፤
ሉቃ. ፩፡ ፳፯።
መ ፩ ኔፊ ፲፡ ፲፫–፳፩።
ሠ ማቴ. ፩፡ ፳፤
ሞዛያ ፲፭፡ ፫።
፲፩ ሀ ኢሳ. ፶፫፡ ፫–፭፤
ሞዛያ ፲፡ ፫–፭።
፲፪ ሀ ፪ ኔፊ ፪፡ ፳፤
አልማ ፲፪፡ ፳፱–፳፭።
ቅ.መ.መ. መስቀል።
ለ ዕብ. ፪፡ ፲፳፤ ፡፡ ፲፭፤
ት. እና ቃ. ፳፪፡ ፩።
፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣
አምላክ።
ለ ሞዛያ ፲፭፡ ፲፪።
ቅ.መ.መ. የኃጢያት ዋጋን
መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ።
፲፡ ሀ ቅ.መ.መ. ዳግመኛ
መወለድን፣ ከእግዚአብሔር
መወለድ።
፲፭ ሀ ፪ ኔፊ ፡፡፡ ፲፳።

መለከተ፣ አዎን፣ እኔ የተናገርኳቸውንም በተመለከተ እምነታችሁ ጠንካራ በመሆኑ ደስታዬ ታላቅ ነው።

፲፱ ከመጀመሪያ ጀምሮ እንደተናገር ኳችሁ፣ እንደ ወንድሞቻችሁ በተደናበረ ሁኔታ እንዳትሆኑ በጣም ፈልጌ ነበር፣ እን ዲሁም የእኔም ፍላጎት አጥጋቢ ሆኖ አግ ኝቼዋለሁ።

፲፱ እናንተ በፅድቅ ጎዳና እንደሆናችሁ ተገንዝቤአለሁና፤ ወደ እግዚአብሔርም መንግስት በሆነው ጎዳና ላይ እንደሆናችሁ እገነዘባለሁ፤ አዎን፣ የእርሱንም [a]ጎዳና የቀና እንደምታደርጉት እገነዘባለሁ።

፳ በጠማማው [a]መንገድ እንደማይራ መድ፣ ከተናገረው ፈቀቅ እንደማይል፣ ከቀኝ ወደ ግራም፣ ወይም ከትክክለኛው ወደተሳሳተው በመዞር ጥላ አንደማይኖረ ውም፣ ስለዚህ ጎዳናውም አንድ ዘለአለማዊ ዙሪያ እንደሆነ በቃሉ ምስክርነት ለእናንተ የታወቀ እንደሆነ ተገንዝቤአለሁ።

፳፩ እናም እርሱ [a]ቅዱስ ባልሆነ መቅደስ ውስጥ አይኖርም፤ የረከሰም ይሁን ንፁህ ያልሆነ ማንኛውም በእግዚአብሔር መን ግስት ተቀባይነት የለውም፤ ስለዚህ ጊዜው ይመጣል፣ አዎን፣ እና ይህም በመጨረሻ ቀን ይሆናል፣ [1]የረከሰው ረክሶ ይቀራል እላ ችኋለሁ።

፳፪ እናም አሁን የተወደዳችሁ ወንድ ሞቼ፣ ወደ እግዚአብሔር ላላችሁ ሀላፊ ነት ስሜታችሁን እቀሰቅሰው ዘንድ፣ በእ ርሱ ፊት እንከን የሌላችሁ በመሆን ትራ መዱ ዘንድ፣ ተቀባይነትንም ባገኛችሁበት በእግዚአብሔር ቅዱሱ ስርዓት ትራመዱ ዘንድ፣ እነዚህን ነግሬአችኋለሁ።

፳፫ እናም አሁን [a]ትሁትና፣ ጨዋና ታዛዥ፣ ሁሉን የምትቀበሉ፣ ታላቅ ፅናት የበዛባችሁና ታጋሽ የሆናችሁ፤ በሁሉም ነገር ራሳችሁን የምትገዙ፣ በሁሉም ጊዜ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ለመጠበቅ ትጉህ፤ የፈለጋችሁትን ነገር በመንፈስም ሆነ በስጋ የምትጠይቁ፣ ለተቀበላችሁትም ማንኛ ውም ነገር ሁልጊዜ ለእግዚአብሔር ምስ ጋና የምትስጡ እንድትሆኑ እፈልጋለሁ።

፳፬ እናም [a]እምነት፣ ተስፋና ልግስና እን ደሚኖራችሁ እርግጠኛ ሁኑ፣ እና ከዚያም ሁልጊዜ መልካም ስራን የምትሰሩ ትሆና ላችሁ።

፳፭ እናም ጌታ ይባርካችሁ፣ ለዘለዓለም በመንግስተ ሰማያት እንድትቀመጡም የእ ነርሱ ልብስ እንከን እንደሌለው የእናንተም እንከን ሳይኖርበት፣ በመጨረሻ ከአብር ሃም፣ ከይስሀቅና፣ ከያዕቆብ፣ እናም ዓለም ስትፈጠር ጀምሮ ከነበሩት ቅዱሳን ነቢያት ጋር ለመቀመጥ እንድትመጡ ዘንድ፣ ልብ ሳችሁን [a]እንከን የለሽ አድርጉት።

፳፮ እናም አሁን የተወደዳችሁ ወንድ ሞቼ፣ እነዚህን ቃላት የተናገርኳችሁ በው ስጤ በሚመሰክረው መንፈስ መሰረት ነው፤ እናም ለቃሌ ታላቅ ትጋት በመስጠታች ሁና በማዳመጣችሁ ነፍሴም እጅግ ሀሴት ታደርጋለች።

፳፯ እናም አሁን፣ [a]የእግዚአብሔር ሰላም እንደ እምነታችሁና መልካም ስራችሁ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እስከዘለዓለም በቤታች ሁና በምድራችሁና፣ በከብቶቻችሁና በመ ንጋዎቻችሁ ላይ እንዲሁም ባላችሁ ንብረ ቶች፣ በሴቶቻችሁ፣ በልጆቻችሁና በራሳ ችሁ ላይ ይሁን። እናም ይህንን ተናግሬአ ለሁ። አሜን።

ምዕራፍ ፳

አልማ በሜሌቅ አስተማረ፣ እናም አጠ መቀ—በአምኒሀ ተቀባይነትን አሳገኘም

፲፱ *ሀ* ማቴ. ፫፡፫።
፳ *ሀ* ፩ ኔፊ ፲፡፲፱፤
አልማ ፴፯፡፲፪፤
ት. እና ቃ. ፫፡፪።
፳፩ *ሀ* ፩ ቆሮ. ፫፡፲፯–፲፯፤ ፮፡፲፱፤
ሞዛያ ፪፡፴፯፤
አልማ ፴፬፡፴፮።
ለ ፩ ኔፊ ፲፭፡፴፫–፴፭፤
፪ ኔፊ ፱፡፲፯፤
ሞር. ፱፡፲፰፤
ት. እና ቃ. ፹፡፳፡፴፭።
፳፫ *ሀ* ቅ.መ.መ. ትሁት፣ ትሕትና።
፳፬ *ሀ* ፩ ቆሮ. ፲፫፤
ኤተር ፲፪፡፴–፴፭፤
ሞሮኒ ፯፡፴፫–፴፯፡፳፡
፳፭ *ሀ* ፪ ጴጥ. ፫፡፲፡
፳፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. ሰላም።

እናም ወጥቶ ሄደ—መልአኩ እንዲመለስና ለህዝቡም ስለ ንስሃ እንዲጮህ አዘዘው—በአሙሌቅ ተቀባይነትን አገኘ፣ እናም ሁለቱ በአሞኒሃ ሰበኩ። በ፲፪፪ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንግዲህ እንዲህ ሆነ አልማ ሊፃፉ ያልቻሉትን ብዙ ነገሮች ለጌዴዎን ህዝብ ካስተማረ፣ የቤተክርስቲያኗን ስርዓት በዛራሔምላ ምድር እንዳደረገው ካቋቋመ በኋላ፣ [ሀ]ከጌዴዎን ምድር ተመለሰ፤ አዎን፣ ካከናወናቸው ስራዎች ራሱን ለማ ሳረፍ በዛራሔምላ ወዳለው ቤቱ ተመለሰ።

፪ እናም በኔፊ ህዝብ ላይ ዘጠነኛ የመሳ ፍንቱ ንግስና በዚሁ ተፈጸመ።

፫ እናም እንዲህ ሆነ በኔፊ ህዝብ ላይ በመ ሣፍንቱ የአስረኛ ዓመት የንግስ ዘመን መጀ መሪያ ላይ አልማ ከዚያ ቦታ ሄደና፣ ጉዞ ውን [ሁ]በሲዶም ወንዝ በስተምዕራብ፣ በም ድረበዳው ዳርቻ በምዕራብ በኩል ወደ ሜሌቅ አደረገ።

፬ እናም እርሱ በተሾመበት በእግዚአ ብሔር [ሂ]ቅዱሱ ስርዓት መሰረት በሜሌቅ ምድር ህዝቡን ማስተማር ጀመረ፤ እናም በሜሌቅ ምድር ሁሉ ህዝቡን ማስተማር ጀመረ።

፭ እናም እንዲህ ሆነ ህዝቡ ከምድረበዳው በምድሪቱ ዳርቻ በኩል ያሉት ሁሉ ወደ እርሱ መጡ። እናም በምድሪቱ ያሉት ሁሉም ተጠምቀው ነበር፤

፮ በሜሌቅ ስራውን በጨረሰ ጊዜ ለቆ ሄደ፣ እናም በሜሌቅ በስተሰሜን በሚገ ኘው ምድር ለሶስት ቀናት ጉዞ አደረገ፤ እናም አሞኒሀ ወደምትባል ከተማ መጣ።

፯ አሁን ምድራቸውንና ከተማቸውን፣ እናም መንደራቸውን፣ አዎን፣ ትናንሽ ከተሞቻቸውንም እንኳን ቢሆን ቦታውን መጀመሪያ በያዘው ሰው ስም መጥራት የኔፊ ህዝብ ልምድ ነበር፤ እናም ይህ ልምድ በአ ሞኒሀ ምድርም የሆነ ነበር።

፰ እናም እንዲህ ሆነ አልማ ወደ አሞኒሀ ከተማ በመጣ ጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል ለእነርሱ መስበክ ጀመረ።

፱ አሁን ሰይጣን በአሞኒሀ ከተማ ያሉትን ሰዎች ልብ በጥብቅ [ለ]ይዞ ነበር፤ ስለሆነም የአልማን ቃል አያዳምጡም ነበር።

፲ ይሁን እንጂ አልማ በከተማ ባሉት ሰዎች ላይ እግዚአብሔር መንፈሱን ያፈሰ ዘንድ [ሐ]በኃያሉ ፀሎቱም ከእግዚአብሔር ጋር [መ]ታገለ፤ በንስሃም ያጠምቃቸው ዘንድ [ሠ]በመንፈስ ብዙ ሰራ።

፲፩ ይሁን እንጂ ልባቸውን አጠጥረው እንዲህ አሉት፥ እነሆ፣ አንተ አልማ መሆንህን እናውቃለን፤ እናም እንደባህ ልህ በብዙ ቦታዎች ባቋቋምካቸው ቤተክ ርስቲያኖች ላይ ሊቀ ካህን መሆንህን እና ውቃለን፤ እኛ ከአንተ ቤተክርስቲያን አይ ደለንም፣ እናም በእነዚህ ዓይነት የሞኞች ባህል አናምንም።

፲፪ እናም አሁን እኛ ከአንተ ቤተክርስቲ ያን ባለመሆናችን በእኛ ላይ ኃይል እንደሌ ለህ እናውቃለን፤ እናም የፍርድ ወንበሩንም [ረ]ለኔፊያህ ሰጥተሀል፣ ስለዚህ በእኛ ላይ ዋና ዳኛ አይደለህም።

፲፫ እንግዲህ ህዝቡ ይህንን በተናገረ ጊዜና ቃሉን ሁሉ በተቃወሙና፣ እርሱ ንም በሰደቡትና፣ ላዩ ላይ በተፉበትና፣ ከከ ተማቸው እንዲወጣ ባደረጉት ጊዜ፣ ከቦ ታው ሄደ፣ እናም ኦሮን ተብላ ወደምት ጠራ ከተማ ጉዞውን አደረገ።

፲፬ እናም እንዲህ ሆነ ሀዘኑ ከብዶት ከቦታ ውም በተጓዘ ጊዜ፣ በአሞኒሀ ከተማ ባሉት ሰዎች ክፋትም ምክንያትም [ሰ]በመከራና በነፍስ ስቃይ ተጓዘ፤ አልማ እንደዚህ በሀ ዘን ጫና እየተጓዘ እያለ እንዲህ ሆነ፣ እነሆ የጌታ [ሸ]መልአክ ታየው፣ እንዲህም አለው፥

ሀ ፩ ሀ አልማ ፪፡ ፳፣ ፯፡ ፲፯።
ለ ፩ ሀ አልማ ፲፯፡ ፲–፳።
ሐ ፩ ሀ ት. እና ቃ. ፲፯፡ ፪–፬። ቅ.መ.መ. የመልከ ጼዴቅ ክህነት።
መ ፩ ሀ ፪ ኔፊ ፳፯፡ ፲፱–፳፪፤ ት. እና ቃ. ፲፡ ፳።
ሠ ፩ ሀ ፪ ኔፊ ፳፯፡ ፩። ቅ.መ.መ. ጸሎት።
ረ ፩ ሀ ኢኖስ ፩፡ ፩–፲፪። ሸ አልማ ፲፯፡ ፲።
ሰ ፩ ሀ ፪ ኔፊ ፳፡ ፲–፲፩። ቅ.መ.መ. መላእክት።

፲፭ አልማ አንተ የተባረክህ ነህ፤ ስለ ዚህ ራስህን አቅና እናም ሀሴትን አድርግ፣ የምትደሰትበት ታላቅ ምክንያት አለህና፤ መልዕክቱንም ከተቀበልክ ከመጀመሪያው ጀምሮ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት በመጠ በቅ ታማኝ በመሆንህ የትልቁ ደስታህ መን ስኤ ሆነህልና። እነሆ ይህንን ለአንተ ᵐየሰ ጠሁህ እኔ ነኝ።

፲፮ እናም እነሆ፣ አንተ ወደ አሞኒሀ ከተማ እንድትመለስና ለከተማው ህዝብ በድጋሚ እንድትሰብክ ለማዘዝ ተልኬአለሁ፤ አዎን፣ ለእነርሱም ስበክ። አዎን፣ ንስሃ ካልገቡ በቀር ጌታ እግዚአብሔር ᵐእንደሚያጠፋ ቸው ንገራቸው።

፲፯ እነሆም፤ በዚህ ጊዜ የህዝባቸውን ነፃ ነት ለማጥፋት ያጠናሉ፣ (ጌታም እንዲህ ብሏልና) ይህም እርሱ ለህዝቡ ከተሰጠው ስርዓት፣ ፍርድና ትዕዛዛት ተቃራኒ ነው።

፲፰ አሁን እንዲህ ሆነ አልማ ከጌታ መላዕ ክት መልዕክቱን ከተቀበለ በኋላ ወደ አሞኒሀ ከተማ በፍጥነት ተመለሰ። እናም ወደ ከተ ማዋ በሌላ መንገድ፣ አዎን በአሞኒሀ ከተማ በስተደቡብ በኩል ገባ።

፲፱ እናም አልማ ወደ ከተማው በገባ ጊዜ ተርቦ ነበር፣ እናም ለአንድ ሰው እንዲህ አለው፥ ለትሁት የእግዚአብሔር አገልጋይ የሚበላውን ትሰጠዋለህን?

፳ እናም ሰውየው እንዲህ አለው፣ እኔ ኔፋውያን ነኝ፣ እናም አንተ የእግዚአብ ሔር ቅዱስ ነቢይ እንደሆንክ አውቃለሁ፣ ᵐመልአኩ በራዕይ ትቀበለዋለህ ያለኝ ሰው አንተን ነህና። ስለዚህ፣ ወደ ቤቴ ከእኔ ጋር ሂድና፣ ምግቤን ከአንተ ጋር እካፈላለሁ፤ እናም ለእኔና ለቤቴ በረከት እንደምትሆን አውቃለሁ።

፳፩ እናም እንዲህ ሆነ ሰውየው በቤቱ ተቀ በለው፤ ሰውየውም ᵐአሙሌቅ ይባል ነበር፤ እናም ዳቦና ስጋን በአልማ ፊት አቀረበለት።

፳፪ እናም እንዲህ ሆነ አልማ ዳቦ በላና ጠገበ፤ እናም አሙሌቅንና ቤቱን ᵐባረከና ለእግዚአብሔር ምስጋናን አቀረበ።

፳፫ እናም ከበላና ከጠገበ በኋላ ለአ ሙሌቅ እንዲህ አለው፥ እኔ አልማ ነኝ፣ እናም በምድሪቱ ላይ ባሉት የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያናት ᵐሊቀ ካህን ነኝ።

፳፬ እናም እነሆ፣ በራዕይና በትንቢት መንፈስ መሰረት በእዚህ ህዝብ ሁሉ መካ ከል የእግዚአብሔርን ቃል ለመስበክ ተጠ ርቻለሁ፤ በዚህም ምድር ነበርኩ እናም እነ ርሱ አልተቀበሉኝም፣ ነገር ግን ᵐአስወ ጡኝ፣ እናም ለዘለአለም ወደዚህች ምድር ጀርባዬን ለመስጠት እያለሁ ነበር።

፳፭ ነገር ግን እነሆ፣ ለዚህ ህዝብ በድጋሚ ተመልሼ እንድተነብይ፣ አዎን እናም ክፋ ታቸውንም በተመለከተ በእነርሱ ላይ እን ድመሰክር ታዝዣለሁ።

፳፮ እናም አሁን፣ አሙሌቅ ስለመገብ ከኝና ስለተቀበልኸኝ የተባረክህ ነህ፤ ለብዙ ቀንም በመፆሜ ተርቤ ነበርና።

፳፯ እናም አልማ ለህዝቡ መስበክ ከመ ጀመሩ በፊት ለብዙ ቀናት ከአሙሌቅ ጋር ቆየ።

፳፰ እናም እንዲህ ሆነ ሰዎቹ በኃጢአታ ቸው አስቀያሚነት እያደጉ ሄዱ።

፳፱ እናም ቃሉም ወደ አልማ እንዲህ ሲል መጣ፤ ሂድ፤ እናም ደግሞ ለአገልጋዬ ለአ ሙሌቅ፣ ለዚህ ህዝብ እንዲህ በማለት ትን ቢት ተናገር በለው—ᵐንስሃ ግቡ፣ ጌታ ንስሃ ካልገባችሁ ይህንን ህዝብ በቁጣ እጎበኘዋ ለሁ ብሏልና፤ አዎን፣ እናም ኃያሉ ቁጣዬ ንም አልመልሰውም።

፴ እናም አልማና አሙሌቅ ከህዝቡ መካ ከል የእግዚአብሔርን ቃል ለማወጅ ሄዱ፤ እናም እነርሱ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው ነበር።

፴፩ እናም በግዞት መያዝ እስከማይ

፲፭ ᵐ ሞዛያ ፳፯፡ ፲፩–፲፯።
፲፯ ᵐ አልማ ፱፡ ፲፪፡ ፲፰፡ ፳፬።
፳ ᵐ አልማ ፲፡ ፣–፱።
፳፩ ᵐ ቅ.መ.መ. አሙሌቅ።
፳፪ ᵐ አልማ ፲፡ ፲፩።
፳፫ ᵐ አልማ ፭፡ ፮፡ ፴፩፡ ፴፱፤ ፲፮፡ ፩–፳።
፳፬ ᵐ አልማ ፳፡ ፲፮።
፳፭ ᵐ አልማ ፱፡ ፲፪፡ ፲፰።
፳፮ ᵐ አልማ ፱፡ ፲፪፡ ፲፰፡ ፲፱፡ ፲፡ ፲–፲፮፡ ፳፡ ፳፩–፳፭ ᵐ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣ ንስሀ መግባት።

ችሉ ድረስ ᐟᐟኃይል ተሰጥቶአቸው ነበር፤ ማንም ሰው ሊገድላቸው አይቻለውም ነበር፤ ይሁን እንጂ በሰንሰለት እስከሚታ ሰሩና ወደ እስር ቤትም እስከሚጣሉ ድረስ ᐞስልጣናቸውን አልተጠቀሙበትም ነበር። አሁን ይህ የተደረገው ጌታ ስልጣኑን በእነ ርሱ እንዲያሳይ ነበር።

፴፪ እናም እንዲህ ሆነ ጌታ በሰጣቸው መንፈስና ኃይል መሰረት ወደ ፊት ሄዱ እናም ለህዝቡ ማስተማርና መተንበይ ጀመሩ።

በአሞኒሀ ምድር ለነበሩት ሰዎች በአልማ፣ ደግሞም በአሙሌቅ የታወጁት ቃላት። እናም በአልማ ዘገባ መሰረት፣ እነርሱ በወህኒ ቤት ተጣሉ፣ እናም በውስጣቸው ባለው ታምራታዊ የእግዚአብሔር ኃይ ልም ተለቀቁ።

ከምዕራፍ ፤ እስከ ፲፬ አጠቃሎ የያዘ።

ምዕራፍ ፤

አልማ የአሞኒሀ ሰዎች ንስሃ እንዲገቡ አዘዘ—ጌታ በመጨረሻው ቀን ለላማናውያን መሀሪ ይሆናል—ኔፋውያን ብርሃኑን ከተዉ፣ በላማናውያን ይጠፋሉ—የእግ ዚአብሔር ልጅ በቅርቡ ይመጣል—ንስሃ የገቡትን፣ የተጠመቁትንና፣ በስሙም ካመኑት ያድናቸዋል። በ፲፪ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም በድጋሚ፣ እኔ አልማ አሙሌ ቅን ለመውሰድና ለህዝቡም፣ ወይም በአ ሞኒሀ ከተማ ላሉት ሰዎች፣ በድጋሚ ለመስ በክ በእግዚአብሔር በመታዘዜ፣ እንዲህ ሆነ ለእነርሱ መስበኬን ስጀምር እንዲህ በማለት ከእኔ ጋር መጣላት ጀመሩ፥

፪ አንተ ማነህ? ምድር ታልፋለች በማለት ለእኛ ቢሰብክም ᐟᐟየአንድን ሰው ምስክርነት እናምናለን ብለህ ትገምታለህን?

፫ እንግዲህ የተናገሩትን ቃላት አልተረ ዱም፤ ምድር እንደምታልፍም አያውቁ ምና።

፬ እናም ደግሞ እንዲህ አሉ፥ ይህች ታላ ቂቱ ከተማ ᐟᐟበአንድ ቀን ትጠፋለች በማለት ብትተነብይም ቃልህን አናምንም።

፭ አሁን እነርሱ ልበ ጠጣርና አንገተ ደን ዳና ሰዎች ስለነበሩ እግዚአብሔር እንደ ዚህ ዓይነት ድንቅ ስራን መስራት ይችላል ብለው አላወቁም።

፮ እናም እንዲህ አሉ፥ እንደዚህ ዓይነቱን ታላቅና ድንቅ እውነታ እንዲናገር በህዝቡ መካከል ከአንድ ሰው በላይ ᐟᐟምንም ስልጣን ሰጥቶ የማይልክ፣ እግዚአብሔር ᐞማን ነው?

፯ እናም እጃቸውን በእኔ ላይ ለመጫን ተነሱ፤ ነገር ግን እነሆ፣ አልነኩኝም። እናም ለእነርሱ ለማወጅ በድፍረት ቆምኩ፣ አዎን፣ በድፍረት እንዲህ በማለት መሰከርኩ፥

፰ እነሆ፣ እናንተ ክፉና ጠማማ ᐟᐟትው ልድ፣ የአባቶቻችሁን ባህል እንዴት ረሳ ችሁ፤ አዎን የእግዚአብሔርንስ ትዕዛዛት እንዴት በፍጥነት ረሳችሁ።

፱ አባታችን ሌሂስ በእግዚአብሔር ᐟᐟእጅ ከኢየሩሳሌም እንደወጣ አታስታውሱምን? ከምድረበዳውስ ሁሉም በእርሱ እንደተ መሩ አታስታውሱምን?

፲ እናም አባቶቻችንን ከጠላቶቻቸው እጅ ምን ያህል ጊዜ እንዳስለቀቀና፣ በወንድሞ ቻቸውም እጅ እንኳን ቢሆን፣ ከመጥፋት እንደጠበቃቸው በፍጥነት ረሳችሁትን?

፲፩ አዎን፣ ለእኛ ባለው ወደር በሌለው ስልጣኑና ምህረቱ፣ እንዲሁም በረዥም ፅናቱ ባይሆን ኖሮ ከዚህ ጊዜ በፊት ከም ድረ ገፅ ሊወገድ በማይቻልበት መጥፋት ይገባን ነበር፣ እናም ምናልባት ᐟᐟመጨረሻ ለሌለው ጉስቁልና ወዮታ እንሰጥ ነበር።

፴፩ ሀ ፩ ኔፊ ፩፡ ፳።
ለ አልማ ፲፡ ፲፯–፳፱።
፴፪ ፪ ሀ ዘዳግ. ፲፯፡ ፮።
፩ ሀ አልማ ፲፯፡ ፴–፲።
፪ ሀ አልማ ፲፡ ፲፪።
ለ ዘፀአ. ፭፡ ፪፣
ሞዛያ ፲፩፡ ፳፯፣
ሙሴ ፭፡ ፲፯።
፫ ሀ አልማ ፲፡ ፲፯–፳፭።
፴ ሀ ፩ ኔፊ ፪፡ ፩–፯።
፲፩ ሀ ሞዛያ ፲፯፡ ፲፩።

፲፪ እነሆ፣ እላችኋለሁ፣ አሁን እርሱ ንስሃ
እንድትገቡ ያዛችኋል፤ እናም እናንተ ንስሃ
ካልገባችሁ በምንም መንገድ የእግዚአብ
ሔርን መንግስት ልትወርሱ አትችሉም።
ነገር ግን እነሆ፣ ይህ ብቻ አይደለም—እርሱ
ንስሃ እንድትገቡ አዟችኋል፣ አለበለዚያም
እናንተን ከምድረ ገፅ ፈፅሞ [ሀ]ያጠፋችኋል፤
አዎን፣ በቁጣውም ይጎበኛችኋል፣ እናም
[ለ]ጽኑ ቁጣው ከእናንተ አይመልስም።
፲፫ እነሆ፣ ትዕዛዛቴን እስከጠበቃችሁ
[ሀ]ድረስ፣ በምድሪቱ ላይ ትበለፅጋላችሁ
ብሎ ለሌሂ የተናገራቸውን ቃላት አታስታ
ውሱምን? እናም በድጋሚም እንዲህ ተብ
ሏል፤ ትዕዛዛቴን እስካልጠበቃችሁ ድረስ
ከጌታ ፊት ትለያላችሁ።
፲፬ እንግዲህ ላማናውያን የእግዚአብሔ
ርን ትዕዛዛት እስካልጠበቁ ድረስ፣ ከጌታ
ፊት [ሀ]እንደተለዩ እንድታስታውሱ እፈል
ጋለሁ። አሁን በዚህ ነገር የጌታ ቃል ማረ
ጋገጫ እንደሆነ እናያለን፣ እናም ላማናው
ያን በምድሪቱ መተላለፍ ከጀመሩበት ጊዜ
አንስቶ ከእርሱ ፊት ተለይተዋል።
፲፭ ይሁን እንጂ እኔ እንዲህ እላችኋለሁ፣
በኃጢአታችሁ ከቀጠላችሁ በፍርድ ቀን
ከእናንተ ይልቅ ለእነርሱ [ሀ]ይቀልላቸዋል፤
አዎን እናም ንስሃ ካልገባችሁ በዚህ ህይወ
ትም ቢሆን እንኳን ለእነርሱ የበለጠ ቀላል
ይሆናል።
፲፮ ለላማናውያን ብዙ የተስፋ ቃል [ሀ]ተሰ
ጥቶአቸዋልና፤ በአባቶቻቸው [ለ]ወግ ምክን
ያት ነው [ሐ]በድንቁርና እንዲቀሩ ስላደረጋ
ቸውና፤ ስለዚህ ጌታ ለእነርሱ መሀሪ ይሆ
ናል፣ እናም በምድሪቱ ላይ ህይወታቸውን
[መ]ያረዝማል።
፲፯ እናም በአንድ ወቅት በቃሉ ወደማመ
ንና፣ የተሳሳተውን የአባቶቻቸውንም ወግ
ወደ መረዳት [ሀ]ይደርሳሉ፤ እናም ብዙዎች
ይድናሉ፣ ጌታ [ለ]ስሙን ለሚጠሩ ሁሉ
መሀሪ ይሆናልና።
፲፰ ነገር ግን እነሆ፣ በኃጢአታችሁ የም
ትቀጥሉ ከሆነ [ሀ]ላማናውያን በእናንተ ላይ
የሚላኩ በመሆናቸው በምድሪቱ ላይ የመቆ
ያችሁ ቀን አይረዝምም፤ ንስሃ የማትገቡም
ከሆነ እናንተ በማታውቁበት ወቅት ይመ
ጣሉ፣ እናም [ለ]ፍፁም በሆነ ጥፋትም ትጎ
በኛላችሁ፤ ይህም በፅኑ የጌታ [ሐ]ቁጣ መሰ
ረት ነው።
፲፱ ህዝቡን ለማጥፋት እናንተ በክፋት
እንድትኖሩ አይፈቅድላችሁም። እኔ ግን
አይሆንም እላችኋለሁ፤ ለጌታ አምላካቸው
ታላቅ ብርሃንን ታላቅ እውቀትን ካገኙ በኋላ
በኃጢያትና በመተላለፍ [ሀ]ለመውደቅ የሚ
ቻላቸው ከሆነ የኔፊ ህዝብ የተባሉትን ሁሉ
ላማናውያን [ለ]እንዲያጠፏቸው ቢፈቅድ
ይሻለዋል።
፳ አዎን፣ በጌታ የተወደዱ ሰዎች ከሆኑ
በኋላ፣ አዎን፣ ከሁሉም ሀገር፣ ነገድ፣ ቋን
ቋና ህዝብ በላይ የተወደዱ ከሆኑ በኋላ፣
ሁሉንም ነገሮች በፍላጎታቸው፣ በእምነ
ታቸው፣ በፀሎታቸው መሰረት፣ ስለነበ
ረው፣ እና ስለሆነው፣ እናም ስለሚመጣው
[ሀ]እንዲያውቁ ከተደረጉ በኋላ፤
፳፩ በእግዚአብሔር መንፈስ ከተጎበኙ
በኋላ፣ ከመልአኩ ጋር ከተነጋገሩ በኋላ፣
የጌታ ድምፅም ከተናገራቸው በኋላና፣ የት
ንቢት መንፈስና የራዕይ መንፈስ፣ ደግሞም
ብዙ ስጦታዎች በልሳን የመናገር ስጦታ፣
እናም የመስበክ ስጦታና፣ የመንፈስ ቅዱስ
ስጦታና [ሀ]የመተርጎም ስጦታ ከተሰጣቸው
በኋላ፤

፲፪ ሀ አልማ ፰፡ ፲፯፤
፲፡ ፲፱፣ ፳፫፣ ፳፯።
ለ አልማ ፰፡ ፳፱።
፲፫ ሀ ፪ ኔፊ ፩፡ ፳፣
ሞዛያ ፩፡ ፯፣
አልማ ፴፯፡ ፲፫።
፲፬ ሀ ፪ ኔፊ ፭፡ ፳–፳፪፤
አልማ ፴፰፡ ፩።
፲፭ ሀ ማቴ. ፲፩፡ ፳፪፣ ፳፬።
፲፯ ሀ አልማ ፲፯፡ ፲፭።
ለ ሞዛያ ፲፡ ፲፪ (ቁጥር ፲፩–፲፯ን
ተመልከቱ)።
ሐ ሞዛያ ፫፡ ፲፩።
መ ሔለ. ፲፭፡ ፲–፲፪።
፲፯ ሀ ኢኖስ ፩፡ ፲፫።
ለ አልማ ፴፰፡ ፭፣
ት. እና ቃ. ፫፡ ፳።
፲፰ ሀ አልማ ፲፯፡ ፪–፫።
ለ አልማ ፲፯፡ ፱።
ሐ አልማ ፳፡ ፳፱።
፲፱ ሀ አልማ ፳፬፡ ፴፤
ለ ፪ ኔፊ ፲፪፡ ፲፭፣ ፲፱–፳፣
አልማ ፶፭፡ ፣–፲፡።
፳ ሀ ቅ.መ.መ. ራዕይ።
፳፩ ሀ ኦምኒ ፩፡ ፳፣
ሞዛያ ፳፡ ፲፫–፲፱፣
፳፫፡ ፲፩–፲፯።

፳፪ አዎን፣ ከኢየሩሳሌም ምድር በጌታ እጅ ᵐበእግዚአብሔር እንዲለቀቁ ከተደረጉ በኋላ፣ ከረሃብ፣ ከበሽታና ከሁሉም ዓይነት ተውሳክ ከዳኑ በኋላ፤ ከዚያም በኋላ እን ዳይጠፉ ለጦርነት በመበርታት ጠነከሩ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ ᵃከባርነት በመውጣትና፣ እስካሁን እንዲቀመጡና እንዲጠበቁ ሆነ ዋል፤ እናም በሁሉም ነገሮች ሀብታም እስ ኪሆኑ ድረስ በልፅገዋል—

፳፫ እናም አሁን እነሆ እንዲህ እላችኋ ለሁ፣ ይህ ህዝብ ብዙ በረከቶችን ከጌታ አግኝቶ ካለው ብርሃንና እውቀት በተቃ ራኒ የሚተላለፍ ከሆነ፣ ይህ ሁኔታ ከሆነ፣ እነርሱም ወደ መተላለፍ የሚወድቁ ከሆነ፣ ከእነርሱ የበለጠ ᵐለላማናውያን የሚቀልላ ቸው ይሆናል እላችኋለሁ።

፳፬ እነሆም፣ የጌታ ᵐቃል ኪዳን ለላማና ውያን ተዘርግቷል፤ ነገር ግን እናንተ የም ትተላለፉ ከሆነ ለእናንተ አይሆኑም፤ ምክ ንያቱም ጌታ እናንተ በእርሱ ላይ የምታምፁ ከሆነ ከምድረ ገፅ ፈፅሞ ትጠፋላችሁ በማ ለት በግልፅ ቃል አልገባምን እንዲሁም በጥብቅ አላወጀምን?

፳፭ እናም አሁን በዚህ የተነሳ፣ እንዳ ትጠፉ ዘንድ፣ መንግስተ ሰማያት ቀርባ ለችና ᵐንስሃ ግቡ በማለት ወደዚህ ህዝብ መሄድ እና መጮህ እንዳለባቸው ለማወጅ ጌታ መልአኩን ብዙ ህዝቦቹን እንዲጎበኝ ልኳል።

፳፮ እናም የእግዚአብሔር ልጅ በክብር በሚመጣበት ቀን ከዚህ በኋላ ᵐሩቅ አይ ደለም፤ እናም ክብሩ የአብ ᵃአንድያ ልጅ ክብር የሆነ፣ ᵇበፀጋ፣ በፍትህና በእውነት፣ በፅናት ᶜመሃሪና በታጋሽነት የተሞላ፣ የህ ዝቡን ጩኸት ᵐለመስማትና መልስ ለመስ ጠት ፈጣን የሆነው ይሆናል።

፳፯ እናም እነሆ፣ በስሙ በማመን ለንስሃ ᵐየሚጠመቁትን ᵃለማዳን ይመጣል።

፳፰ ስለዚህ፣ የጌታን መንገድ አዘጋጁ፣ በነበሩበት መሰረት ሰዎች በሙሉ ᵐየስራ ቸውን ውጤት የሚሰበስቡበት ጊዜ ቀር ቧልና—ᵃፃድቃን ከሆኑ በኢየሱስ ክርስቶስ ሀይልና መድሀኒት መሰረት የነፍሳቸውን ደህንነት ᵃያጭዳሉ፤ እናም ክፉ ከሆኑ በዲ ያብሎስ ስልጣንና ግዞት መሰረት ለነፍሳ ቸው ᵇእርግማንን ያጭዳሉ።

፳፱ አሁን እነሆ፣ ይህ ወደ ህዝቡ የሚ ጮኸው የመልአክ ድምፅ ነው።

፴ እናም አሁን፣ ᵐየተወደዳችሁ ወንድ ሞቼ፣ እናንተ ወንድሞቼ ናችሁና፣ እናም የተወደዳችሁ መሆን ይገባችኋል፣ ለን ስሃ የሚሆን ስራን መስራትም አለባችሁ፣ ምክንያቱም ልባችሁ በጌታ ቃል ላይ እጅግ ጠጥሯልና እናም ᵃየተሳሳታችሁና የወደቃ ችሁ ህዝቦች ናችሁ።

፴፩ አሁን እንዲህ ሆነ እኔ አልማ እነዚህን ቃላት ስናገር፣ እነሆ፣ ህዝቡ በእኔ ተቆጥ ቷል ምክንያቱም እነርሱ ልበ ጠጣር እና ᵐአንገተ ደንዳና ሰዎች እንደሆኑ ነግሬአ ቸዋለሁና።

፴፪ እናም ደግሞ የጠፉና የወደቁ ሰዎች መሆናቸውን በመናገሬ፣ በእኔ ተቆጡ፣ እናም ወደ ወህኒ ቤት ይጥሉኝ ዘንድ እጃ ቸውን ሊጭኑብኝ ፈለጉ።

፴፫ ነገር ግን እንዲህ ሆነ ጌታ በዚያን ጊዜ እኔን ወስደው ወህኒ ቤት እንዲጥሉኝ አል ፈቀደላቸውም ነበር።

፴፬ እናም እንዲህ ሆነ አሙሌቅ ሄደና ወደፊት ቆሞ፣ ደግሞም መስበክ ጀመረ። እናም አሁን ᵐየአሙሌቅ ቃላት በሙሉ አልተፃፉም፣ ይሁን እንጂ ከቃሉ የተወሰ ነው ክፍል በዚህ መፅሐፍ ተፅፏል።

፳፪ ᵍ ፪ ኔፊ ፩፡፱።
ᵃ ሞዛያ ፳፯፡፲፯።
፳፫ ᵍ ማቴ. ፲፩፡ ፳፪–፳፱።
፳፬ ᵍ ፪ ኔፊ ፴፡ ፱–፮፤
ት.እና ቃ. ፫፡ ፳።
፳፭ ᵍ አልማ ፯፡ ፱፣
ሔለ. ፭፡ ፴፪።
፳፮ ᵍ አልማ ፯፡ ፯።
ᵃ ቅ.መ.መ. አንድያ ልጅ።
ᵇ ቅ.መ.መ. ጸጋ።
ᶜ ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።
ᵈ ዘዳግ. ፳፭፡ ፯።
፳፯ ᵍ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣
መጥመቅ።
ᵃ ቅ.መ.መ. ቤዛ፣ ማዳን፣
ቤዛነት።
፳፰ ᵍ ት.እና ቃ. ፭፡ ፲፣ ፮፡ ፴፫።
ᵃ መዝ. ፯፡ ፲፯።
ᵇ ሐ ቅ.መ.መ. ኩነኔ።
ᶜ ᵍ ፩ ዮሐ. ፪፡ ፲፩።
ᵈ አልማ ፲፪፡ ፳፪።
ᵉ ᵍ ፪ ኔፊ ፳፭፡ ፳፰፣
ሞዛያ ፫፡ ፲፡፡
ᶠ ᵍ አልማ ፲።

ምዕራፍ ፲

ሌሂ ከምናሴ የዘር ሐረግ ነው—አሙሌቅ ለአልማ የሆነውን መለኮታዊ ትዕዛዝ አወሳ—የፃድቃኖች ፀሎት ህዝቡ እንዲ ድኑ ያደርጋል—ፃድቅ ያልሆኑት ጠበቆች እና ዳኞች ለህዝቡ ጥፋት መሰረትን ይጥ ላሉ። በ፳፪ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እንግዲህ እነዚህ በአሞኒሀ ምድር ለነበ ሩት ሰዎች [ሀ]አሙሌቅ እንዲህ በማለት የሰ በካቸው [ለ]ቃላት ናቸው፡፡

፪ እኔ አሙሌቅ ነኝ፤ የአሚናዲ የዘር ሐረግ የሆነው የእስማኤል ልጅ የሆነው የጊዶናን ልጅ ነኝ፤ እናም ይኸው እራሱ አሚናዲ ነበር በእግዚአብሔር እጅ በቤ ተመቅደሱ ግድግዳ ላይ የተፃፈውን የተ ረጎመው።

፫ እናም አሚናዲ የኔፊ የዘር ሐረግ፣ ከኢ የሩሳሌም ምድር የወጣው፣ [ሁ]የምናሴ የዘር ሐረግ የሆነው የሌሂ ልጅ ነበር፣ እርሱም በወንድሞቹ እጅ [ለ]ወደግብፅ የተሸጠው [ሐ]የዮሴፍ ልጅ ነበር።

፬ እናም እነሆ፣ እኔን በሚያውቁኝ ሰዎች ሁሉ መካከል ትንሽ ዝና ያለኝ ሰው አይደ ለሁም፤ አዎን፣ እናም እነሆ ብዙ ነገድና፣ [ሁ]ወዳጆች አሉኝ፤ ታታሪ ሆኜ በመስራትም ደግሞ ብዙ ሀብትን አፍርቻለሁ።

፭ ይሁን እንጂ፣ ከዚህ ሁሉ በኋላ፣ የጌ ታን መንገድ እናም [ሁ]ሚስጥሩንና ድንቅ ኃይሉን ብዙም አላውቅም ነበር። እነዚህን ነገሮች ብዙም አላውቅም እላለሁ፤ ነገር ግን እነሆ፣ ስህተተኛ ነኝ፣ የእርሱን ሚስጥሮ ችና አስደናቂ ሀይል አይቻለሁና፤ አዎን፣ እንዲሁም የዚህን ሕዝብ ሕይወት ሲጠ ብቅም።

፮ ይሁን እንጂ፣ ብዙ ጊዜ [ሁ]ተጠርቼ [ለ]ባለ መስማቴ ልቤን አጠጥሬ ነበር፤ ስለዚህ እነ ዚህን ነገሮች በተመለከተ አወቅሁ፤ ሆኖም ይህን ለማወቅም አልፈቀድኩም፤ ስለዚህ በልቤ ክፋት በመሳፍንቱ አስረኛ ዓመት የንግስ ዘመን እስከ ሰባተኛው ወር አራተኛ ቀንም ድረስ እንኳን በእግዚአብሔር ላይ ለማመፅ ሄድኩ።

፯ የቅርብ ዘመዴን ለማየት በተጓዝኩ ጊዜ፣ እነሆ የጌታ [ሀ]መልአክ ታየኝና እንዲህ አለኝ፥ አሙሌቅ የጌታን ነቢይ፣ አዎን፣ ቅዱሱን ሰው፣ በእግዚአብሔር የተመረ ጠውን ሰው፣ ምግብን ትመግበዋለህና ወደ ራስህ ቤት ተመለስ፤ በዚህ ህዝብ ኃጢያት የተነሳ ለብዙ ቀናት [ለ]ጾሟል፣ ተርቧልም፣ እናም በቤትህ [ሐ]ተቀብለህ መግበው፣ እር ሱም አንተንና ቤትህን ይባርካል፤ እናም የጌታ በረከት በአንተና በቤትህ ላይ ይሆ ናል።

፰ እናም እንዲህ ሆነ ለመልአኩም ድምፅ ታዘዝኩና፣ ወደ ቤቴ ተመለስኩ። እናም በምሄድበት ጊዜ መልአኩ በቤትህ ትቀበ ለዋለህ ሲል የተናገረኝን [ሀ]ሰው አገኘሁት—እናም እነሆ ይህም የእግዚአብሔርን የሆ ኑትን በተመለከተ ሲያናገራችሁ የነበረው ሰው ራሱ ነበር።

፱ እናም መልአኩ እርሱ [ሀ]ቅዱስ ሰው ነው አለኝ፤ ስለዚህ በእግዚአብሔር መልአክ የተነገረ ስለሆነ ቅዱስ መሆኑን አውቃለሁ።

፲ እናም በድጋሚ፣ እርሱ የመሰከራቸው ነገሮች እውነት መሆናቸውን አውቃለሁ፤ እነሆም እንዲህ እላችኋለሁ፣ ጌታ ሕያው እንደሆነ እነዚህን ነገሮች ለእኔ ለመግለፅ [ሀ]መልአኩን ልኳል፤ እናም እርሱ ይህ ንን ያደረገው አልማ በእኔ ቤት [ለ]በቆየበት ወቅት ነው።

፲፩ እነሆም፣ ቤቴን ባርኳል፣ እኔን፣

፲ ፩ ሀ አልማ ፰፡ ፳፩–፳፱።
ለ አልማ ፱፡ ፴፩።
፲ ሀ ዘፍጥ. ፵፩፡ ፶፩፤ ፩ ዜና ፱፡ ፲።
ለ ዘፍጥ. ፴፯፡ ፳፱–፴፯።
ሐ ቅ.መ.መ. ዮሴፍ፣ የያዕቆብ ልጅ።

፬ ሀ አልማ ፲፫፡ ፲፮።
፭ ሀ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ሚስጥሮች።
፮ ሀ አልማ ፭፡ ፴፯።
ለ ት.እና ቃ. ፴፱፡ ፱።
፯ ሀ አልማ ፰፡ ፳።
ለ አልማ ፭፡ ፴፮፤ ፮፡ ፮።

ቅ.መ.መ. ጾም፣ መጾም።
ሐ የሐዋ. ፲፡ ፴–፴፭።
፰ ሀ አልማ ፰፡ ፲፱–፳፭።
፱ ሀ ቅ.መ.መ. ቅዱስ።
፲ ሀ አልማ ፲፭፡ ፴–፴፭።
ለ አልማ ፰፡ ፳፯።

ሚስቴን፣ ልጆቼንና፣ አባቴን እናም ዘመዶቼን [ሀ]ባርኳል፤ አዎን፣ ዘሮቼን በሙሉ ባርኳል፣ እናም ጌታ በተናገረው ቃል መሰረት በረከቱ በእኛ ላይ ሆኗል።

፲፪ እናም አሁን፣ አሙሌቅ እነዚህን ቃላት በተናገረ ጊዜ፣ እነርሱ የተከሰሱባቸውን ነገሮች እናም ደግሞ በውስጣቸው ባለው የትንቢት መንፈስ ስለሚመጡት ነገሮቹ የሚመሰክሩ [ሀ]ከአንድ ምስክር በላይ እንዳለ በመመልከታቸው ህዝቡ መገረም ጀመረ።

፲፫ ይሁን እንጂ፣ በተንኮል [ሀ]ስራቸው በቃላቸው ይይዟቸው ዘንድ፣ በእነርሱም ላይ ምስክር ያገኙባቸው ዘንድ፣ በህግ መሰረት እንዲፈረድባቸው ወደ ዳኛዎቻቸው አሳልፈው ይሰጧቸው ዘንድ፣ እና በሚያስመስሉት ወይም በእነርሱ ላይ በሚመሰክሩባቸው ወንጀል መሰረት እንዲገደሉ ወይም ወደ እስር ቤት እንዲጣሉ ዘንድ እነርሱን ለመጠየቅ ያሰቡ በመካከላቸው አንዳንድ ነበሩ።

፲፬ አሁን እነዚህ [ሀ]ጠበቆች የነበሩት፣ በፍርድ ጊዜ በዳኞቹ ፊት በወንጀሉ ህጉን እንዲዳኙ በህዝቡ የተቀጠሩት፣ እንዲሁም የተሾሙት ሰዎች ሊያጠፏቸው ሲፈልጉ የነበሩ ናቸው።

፲፭ አሁን እነዚህ ጠበቆች የህዝቡን ጥበብና ሴራ ሁሉ የተማሩት ናቸው፣ እናም ይህ በሙያቸው ባለሙያ እንዲሆኑ እንዲያስችላቸው ነው።

፲፮ እናም እንዲህ ሆነ አሙሌቅን ቃሉን እንዲያጥፍ ያደርጉት ዘንድ ወይም ለሚናገረው ተቃራኒ ይሆኑ ዘንድ ይጠይቁት ጀመር።

፲፯ እንግዲህ አሙሌቅ ዕቅዳቸውን ለማወቅ እንደሚችል አያውቁም። ነገር ግን እንዲህ ሆነ እርሱን መጠየቅ ሲጀምሩ፣ ሀሳባቸውን [ሀ]ገመተ እናም እንዲህ አላቸው፥ እናንተ ክፉና ጠማማ [ለ]ትውልድ፣ ጠበቆች እና ግብዞች፣ የዲያብሎስን መሰረት እየመሰረታችሁ ናችሁና፤ የእግዚአብሔርን ቅዱሳን ለመያዝ መያዣና [ሐ]ወጥመድ ዘርግታችኋልና።

፲፰ የፃድቃኖችን መንገድ [ሀ]ለማጣመም፣ እናም የእግዚአብሔርን ቁጣ በራሳችሁ ላይ እንዲመጣ ለማድረግ፣ ለዚህ ህዝብ ፍፁም ጥፋት እንኳን ዕቅድ አዘጋጅታችኋል።

፲፱ አዎን፣ የመጨረሻው ንጉሳችን ሞዛያ የሚሾመው ማንም የለምና፣ ይህ ህዝብም በራሱ ድምፅ እንዲመራ በማድረግ መንግስቱን ለመስጠት በተቃረበበት ወቅት፣ በጥሩ ሁኔታ እንዲህ ብሏል—አዎን፣ እርሱ ጥሩ ተናግሯል፣ የዚህ ህዝብ ድምፅ ክፋትን [ሀ]የሚመርጥበት ጊዜው መምጣት ካለበት፣ ይህም ማለት ህዝቡ በመተላለፍ የሚወድቅበት ጊዜው የሚመጣ ከሆነ ለጥፋትም ይደርሳሉ።

፳ እናም አሁን እንዲህ እላችኋለሁ፣ ጌታ ክፋታችሁን በጥሩ ሁኔታ ይፈርዳል፤ በተገቢው ሁኔታም ለህዝቡ [ሀ]በመልአኩ ድምፅ፤ ንስሃ ግቡ፣ ንስሃ ግቡ መንግስተ ሰማያት ቀርባለችና በማለት ይጮሀል።

፳፩ አዎን፣ በመልአኩ ድምፅ በተገቢው ሁኔታ እንዲህ በማለት ይጮሀል፥ በህዝቤ መካከል ፍትህንና ፍርድን በእጄ ይዤ [ሀ]እመጣለሁ።

፳፪ አዎን፣ እናም በምድሪቱ አሁን ባሉት [ሀ]ፃድቃኖች ፀሎት ባይሆን ኖሮ፣ ፍፁም በሆነው ጥፋቱ አሁን ይጎበኛችሁ ነበር እላለሁ፤ ይሁን እንጂ በኖህ ጊዜ እንደነበሩት ሰዎች [ለ]በጥፋት ውሀ አይሆንም፣ ነገር ግን በረሃብና፣ በቸነፈር እንዲሁም በጎራዴ ይሆናል።

፲፩ ሀ አልማ ፰፥፳፪።
፲፪ ሀ አልማ ፱፥፮።
፲፫ ሀ አልማ ፲፩፥፳፩።
፲፬ ሀ አልማ ፲፥፳፬፤ ፲፩፥፳–፳፩፤ ፲፬፥፲፰።
፲፯ ሀ አልማ ፲፪፥፫፤ ፲፰፥፳፤ ፴፪፤ ት. እና ቃ. ፮፥፲፮።
ለ ማቴ. ፫፥፯፤
አልማ ፱፥፰።
ሐ ት. እና ቃ. ፲፥፳፩–፳፯።
፲፰ ሀ የሐዋ. ፲፫፥፲።
፲፱ ሀ ሞዛያ ፳፱፥፳፯፤ አልማ ፪፥፫–፯፤ ሔለ. ፭፥፪።
፳ ሀ አልማ ፰፥፲፬–፲፮፤ ፲፫፥፳፪።
፳፩ ሀ ሞዛያ ፲፫፥፴፬።
፳፪ ሀ ያዕ. ፭፥፲፮፤ ሞዛያ ፳፯፥፲፬–፲፮።
ለ ዘፍጥ. ፰፥፳፩፤ ፫ ኔፊ ፳፪፥፰–፲።
ቅ.መ.መ. የኖኅ ዘመን የጥፋት ውሀ።

፳፫ ነገር ግን በፃድቃኖች [ሀ]ፀሎት ድናችኋል፤ አሁንም ስለዚህ ፃድቃኖችን ከመካከላችሁ ከጣላችሁ ጌታ እጁን አያሳርፍም፤ ነገር ግን በኃያሉ ቁጣው በእናንተ ላይ ይመጣል፤ በረሃብና በቸነፈር እንዲሁም በጎራዴ ትመታላችሁ፤ እናም ንስሃ ካልገባችሁ በቀር [ለ]ጊዜው ቀርቧል።

፳፬ እናም አሁን እንዲህ ሆነ ህዝቡ ይበልጥ በአሙሌቅ ተቆጣ፣ እናም እንዲህ በማለትም ጮኹ፥ ጻድቅ በሆነው ህጋችን ላይ፣ እናም በመረጥናቸው በብልሁ ጠበቃዎቻችን ላይ ይህ ሰው ክፉን ይናገራል።

፳፭ ነገር ግን አሙሌቅ እጁን ዘረጋ፣ እናም በኃይል እንዲህ በማለት ጮኸ፥ አቤቱ እናንተ ክፉና ጠማማ ትውልድ፣ ሰይጣን ለምን በልባችሁ ትልቅ ቦታን ይይዛል? ለምንስ በእናንተ ላይ እንደእውነቱ የተነገሩትን ቃላት እንዳትረዱ [ሀ]ዐይናችሁን ለማሳወር ስልጣን እንዲኖረው ራሳችሁን ትሰጡታላችሁ?

፳፮ እነሆም በህጋችሁ ተቃራኒን መስክሬ አለሁን? እናንተም አትረዱም፤ ከህጋችሁ ተቃራኒን ተናግረሃል ትላላችሁ፤ ነገር ግን እኔ አልተናገርኩም፣ ነገር ግን ህጋችሁን በመደገፍ ኩነኔአችሁን ተናግሬአለሁ።

፳፯ እናም አሁን እነሆ፣ እንዲህ እላችኋለሁ፣ የዚህ ህዝብ ጥፋት መሰረቱ ፃድቃን ባልሆኑት [ሀ]ጠበቃዎቻችሁና ዳኞቻችሁ መጣል ጀምሯል።

፳፰ እናም አሁን እንዲህ ሆነ አሙሌቅ እነዚህን ቃላት በተናገረ ጊዜ ህዝቡ እንዲህ በማለት በእርሱ ላይ ጮኸ፥ አሁን ይህ ሰው የዲያብሎስ ልጅ እንደሆነ እናውቃለን እኛን [ሀ]ዋሽቶናልና፤ ከህግጋቶቻችንም ተቃራኒ የሆነውን ተናግሯልና። እናም አሁን ይህን አለመቃረኑን ይናገራል።

፳፱ እናም በድጋሚ፣ ጠበቆቻችንና ዳኞቻችንን አጥብቆ ነቅፏል።

፴ እናም እንዲህ ሆነ እነዚህን ነገሮች በእርሱ ላይ እንዲያስታውሱ ጠበቆቹ በልባቸው አስቀመጡት።

፴፩ እናም ከእነርሱ መካከል ዚኤዝሮም የሚባል አንድ ሰው ነበር። ከእነርሱ መካከል ዋና ባለሙያ በመሆን በህዝቡም መካከል በርካታ እንቅስቃሴዎችን ስለነበረው አሙሌቅንና አልማን [ሀ]ለመክሰስ ግንባር ቀደም ነበር።

፴፪ አሁን የጠበቆቹ ዓላማ ገንዘብ ለማግኘት ነበር፤ እናም በተቀጠሩበት መሰረትም ገንዘብን ያገኛሉ።

ምዕራፍ ፲፩

የኔፋውያን የገንዘብ አያያዝ ተገለፀ—አሙሌቅ ከዚኤዝሮም ጋር ተጣላ—ክርስቶስ ሰዎችን ከነኃጢአታቸው አያድናቸውም—መንግስተ ሰማያትን የሚወርሱት ብቻ ይድናሉ—ሰዎች ሁሉ በህያውነት ይነሳሉ—ከትንሳኤ በኋላ ሞት የለም። በ፹፪ ም.ዓ. ገደማ።

፩ አሁን ማንኛውም ሰው የህጉ ዳኛ የሆነ፣ ወይም ዳኛ በመሆን የተሾሙት ለፍርድ በቀረቡት ላይ ለመፍረድ በሚሰሩበት ሰዓት መሰረት ደሞዝ ያገኙ ዘንድ የሞዛያ ህግ ነበር።

፪ አሁን አንድ ሰው በሌላው ባለእዳ ከሆነ፣ እናም ያለበትንም እዳ ካልከፈለ፣ ለዳኛው አቤቱታ ይቀርብበታል፤ እናም ዳኛው ስልጣኑን ተግባራዊ ያደርጋል፤ በፊቱ እንዲያቀርቡት ሹሞችን ይልካልም፣ እናም በህጉና በእርሱ ላይ በቀረቡት መረጃዎች መሰረት ይፈርድበታል፣ ሰውየው ያለበትን እዳ እንዲከፍል ይገደዳልም፣ አለበለዚያ ንብረቱ ይወሰድበታል፣ ካልሆነም ከህዝቡ መካከል ቀማኛና ሌባ በመባል ይጣላል።

፫ እናም ዳኛው በሰራበት መጠን ክፍያውን ይቀበላል—ለቀን አንድ ሰኒን ወርቅ፣ ወይም ከሰኒን ወርቅ እኩል የሆነ አንድ

፳፫ ሀ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
ለ አልማ ፴፬፥ ፴፪–፴፫።
፳፭ ሀ ፪ ቆሮ. ፬፥ ፬፤
አልማ ፲፬፥ ፮።
፳፯ ሀ ሉቃ. ፲፩፥ ፵፫–፶፪።
፳፰ ሀ አልማ ፲፬፥ ፪።
፴፩ ሀ አልማ ፲፩፥ ፳–፴፮።

ሴነም ብር፤ ይህም በተሰጠው ህግ መሰ
ረት ነው።

፬ አሁን እነዚህ የተለያዩት ቁራጭ ወርቆ
ቻቸው እናም ብሮቻቸው በዋጋቸው መሰ
ረት ስማቸው ናቸው። እናም ስሞቹም የተ
ሰጡት በኔፋውያን ነው፣ በኢየሩሳሌም እን
ደነበሩት በአይሁድ አቆጣጠር አልተሰየ
ሙም ነበርና፤ ወይም እንደ አይሁዶችም
አለካክ አልለኩዋቸውም ነበር፤ ነገር ግን
ስያሜያቸውንና መለኪያቸውን በመሳፍ
ንት ንግስና ጊዜ በንጉስ ሞዛያ "እስኪቋ
ቋሙ ድረስ በህዝቡ አስተሳሰብ እና ጉዳ
ዮች መሰረት በማንኛውም ትውልድ ይቀ
ይሯቸው ነበር።

፭ አሁን አቆጣጠሩ ይህ ነው—አንድ
ሰኒን ወርቅ፣ አንድ ሴን ወርቅ፣ አንድ ሹም
ወርቅና አንድ ሊምና ወርቅ ነው።

፮ አንድ ሴነም ብር፣ አንድ አምኖር ብር፣
አንድ ኤዝረም ብር፣ እናም አንድ ኦንቲ
ብር ነው።

፯ አንድ ሲነም ብር ከአንድ ሲነን ወርቅ
ጋር እኩል ነበር፣ እናም ለአንድ መለኪያ
ገብስና፣ ደግሞ ለሁሉም ዓይነት እህል ለአ
ንድ መለኪያ ዋጋ ነበር።

፰ አሁን የአንድ ሴኦን ወርቅ መጠን ከሁ
ለት ሲነን ወርቅ ዋጋ ጋር እኩል ነው።

፱ እናም አንድ ሹም ወርቅ ከሁለት ሲኦን
ወርቅ ጋር ዋጋው እኩል ነበር።

፲ እናም አንድ ሊምና ወርቅ የሁሉም ዋጋ
ድምር ነበር።

፲፩ እናም አንድ አምኖር ብር ትልቅነቱ
ከሁለት ሴነም እኩል ነው።

፲፪ እናም አንድ ኤዝረም ብር ትልቅነቱ
አራት ሲነም ያህል ነበር።

፲፫ እናም አንድ ኦንቲ ከሁሉም ድምር
ጋር እኩል ነው።

፲፬ አሁን ይህ የአቆጣጠራቸው የትንሹ
ቁጥር ዋጋ ነው—

፲፭ አንድ ሺብሎን የአንድ ሲነም ግማሽ
ነው፤ ስለዚህ፣ አንድ ሺብሎን የግማሽ
ገብስ መለኪያ ዋጋ ነው።

፲፮ እናም አንድ ሽብለም ግማሽ ሺብሎን
ነው።

፲፯ እናም አንድ ልህ ግማሽ ሽብለም ነው።

፲፰ አሁን በአቆጣጠራቸው መሰረት ይህ
ቁጥራቸው ነው።

፲፱ አሁን አንድ አንተአን ወርቅ ከሶስት
ሽብሎን ጋር እኩል ነው።

፳ እንግዲህ ይህን ገንዘብ ለማግኘት ብቻ
ነበር፣ ምክንያቱም ደሞዛቸውን እንደስራ
ቸው አግኝተዋልና፤ ስለዚህ፣ ገንዘብ በፊ
ታቸው በመጡት አቤቱታ መሰረት "ያገኙ
ዘንድ ሕዝቡን ለርበሻዎችና ለሁሉም አይ
ነት ሁከታዎች እና ክፋት አውከዋቸዋል፤
ስለዚህ ህዝቡን በአልማና በአሙሌቅ ላይ
አነሳስተዋል።

፳፩ እናም ይህ ዚኤዝሮም አሙሌቅን እን
ዲህ በማለት መጠየቅ ጀመረ፡ እኔ የምጠይ
ቀውን ጥቂት ጥያቄዎች ትመልስልኛለህን?
አሁን ዚኤዝሮም መልካም የሆነውን ያጠፋ
ዘንድ በዲያብሎስ "ዕቅድ ባለሟል ነበር፤
ስለዚህ፣ ለአሙሌቅም አለው፡ በአንተ ላይ
የማደርገውን ጥያቄዎች ትመልሳለህን?

፳፪ እናም አሙሌቅ እንዲህ አለው፡ በእኔ
ውስጥ ባለው "በጌታ መንፈስ መሰረት ከሆነ፣
አዎን፤ ከጌታ መንፈስ ተቃራኒ የሆነ ምንም
አልናገርምና። እናም ዚኤዝሮም እንዲህ
አለው፣ እነሆ ስድስቱ የብር ኦንቲዎች እነ
ዚህ ናቸው፣ እናም የኃያሉን ፍጡር መኖር
የምትክድ ከሆነ ይህንን በሙሉ እሰጥሃለሁ።

፳፫ አሁን አሙሌቅ እንዲህ አለ፡ አንተ
"የሲኦል ልጅ፣ ለምን "ትፈትነኛለህ? ፃድ
ቃን እንደዚህ ላለ ፈተና የማይበገሩ እንደ
ሆነ አታውቅምን?

፳፬ እግዚአብሔር እንደሌለስ ታምናለ
ህን? እኔ እንዲህ እልሃለሁ፣ አይሆንም፣
እግዚአብሔር እንዳለ ታውቃለህ፣ ነገር ግን
ከእርሱ የበለጠ "ገንዘብ ስለምትወድ ነው።

፲፩ ፬ ሀ ሞዛያ ፳፱፡ ፣–፣፬።
፳ ሀ አልማ ፲፡ ፴፪።
፳፩ ሀ አልማ ፲፡ ፲፫።

፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
፳፫ ሀ አልማ ፭፡ ፣፩።
ለ ቅ.መ.መ. መፈተን፣ ፈተና።

፳፬ ሀ ፩ ጢሞ. ፮፡ ፲፣
ቲቶ ፩፡ ፲፩።

፳፭ እናም አሁን በእግዚአብሔር ፊት ዋሽተኸኛል። ከእኔም እነርሱን ለማስቀ ረት በልብህ ባሰብህ ጊዜ፣ ለእኔም፣ እነሆ ታላቅ ዋጋ ያላቸውን እነዚህን ስድስት ኦን ቲዎች፣ እሰጥሀለሁ ብለኸኛል፤ እናም እኔን ታጠፋኝ ዘንድ ምክንያት እንዲሆንህ እውነ ተኛና ህያው የሆነውን እግዚአብሔርን እን ድክድ ትፈልጋለህ። እናም አሁን እነሆ፣ ለዚህ ለታላቅ ጥፋት ዋጋህን ታገኛለህ።

፳፮ እናም ዚኤዝሮም እንዲህ አለው፡ እውነተኛና ህያው እግዚአብሔር አለ ትላ ለህን?

፳፯ እናም አሙሌቅ እንዲህ አለ፡ አዎን፣ እውነተኛና ህያው እግዚአብሔር አለ።

፳፰ አሁን ዚኤዝሮም እንዲህ አለ፡ ከአ ንድ አምላክ በላይ አለን?

፳፱ እናም እርሱ የለም ሲል መለሰለት።

፴ አሁን ዚኤዝሮም በድጋሚ እንዲህ አለ፡ እነዚህን ነገሮች እንዴት ታውቃለህ?

፴፩ እናም እንዲህ አለ፤ [ሀ]መልአኩ እነዚ ህን እንዳውቃቸው አደረገኝ።

፴፪ እናም ዚኤዝሮም በድጋሚ እንዲህ አለ፣ የሚመጣው ማን ነው? የእግዚአብ ሔር ልጅ ነውን?

፴፫ እናም እርሱ አዎን አለው።

፴፬ እናም ዚኤዝሮም በድጋሚ እንዲህ አለ፡ ህዝቡን [ለ]በጋጢአታቸው ያድናቸዋ ልን? አሙሌቅም መለሰ፣ እናም አለው፡ ይህን አያደርግም እልሀለሁ፣ ምክንያቱም ቃሉንም ለመካድ አይቻለውምና።

፴፭ እንግዲህ ዚኤዝሮም ለህዝቡ እንዲህ አለ፡ እነዚህን ነገሮች ታስታውሱ ዘንድ ተመልከቱ፤ እግዚአብሔርንም ለማዘዝ ስልጣን ያለው ይመስል—አንድ ብቻ አም ላክ አለ ብሏልና፤ ይሁን እንጂ የእግዚአ ብሔር ልጅ ይመጣልም ብሏል፣ ነገር ግን ህዝቡን አያድንም ብሎ ተናግሯል።

፴፮ እንግዲህ አሙሌቅ በድጋሚ እንዲህ አለው፡ እነሆ አንተ ዋሽተሀል፣ ሰዎችንም በጋጢአታቸው አያድንም በማለቴ እግዚ አብሔርን ለማዘዝ ስልጣን እንዳለኝ ተናገ ርኩ ብለሃል።

፴፯ እናም በድጋሚ እንዲህ እልሃለሁ [ሐ]ከነጋጢአታቸው ሊያድናቸው አይች ልም፤ እኔም ቃሉን መካድ አይቻለኝ ምና፣ እናም [ሰ]ምንም እርኩስ ነገር [ሠ]መን ግስተ ሰማያትን ሊወርስ አይችልም ብሏ ልና፤ ስለዚህ፣ መንግስተ ሰማያትን ካል ወረስህ እንዴት ልትድን ትችላለህ? ስለዚህ ከነጋጢያትህ መዳን አትችልም።

፴፰ አሁን ዚኤዝሮም በድጋሚ እንዲህ አለው፡ የእግዚአብሔር ልጅ እውነተኛ ዘለአለማዊ አባት ነውን?

፴፱ እናም አሙሌቅ እንዲህ አለው፡ አዎን፣ እርሱ የሰማይና የምድር፣ እናም በእነርሱም ያሉት [ሀ]ሁሉም ነገሮች እውነ ተኛ [ለ]ዘለአለማዊ አባት ነው፤ እርሱ የመ ጀመሪያና የመጨረሻ፣ የፊተኛውና የኋለ ኛው ነው፤

፴ እናም ህዝቡን [ሀ]ለማዳንና ወደ [ለ]ዓለም ይመጣል፤ በስሙ ለሚያምኑም መተላለ ፋቸውን [ሐ]በራሱ ላይ ይወስዳል፤ እነዚህም ዘለዓለማዊ ህይወት ያላቸው ናቸው፣ እናም ደህንነት ለሌላ ለማንም አይመጣም።

፴፩ ስለዚህ ለጋጢአተኞች የሞት እስር ከመፈታት በስተቀር [ሀ]ቤዛነት እንዳልተ ፈፀመ ሆነው ይቆያሉ፤ እነሆም፣ ሁሉም ከሞት [ለ]የሚነሱበት፣ እናም ከእግዚአብ ሔር ፊት የሚቆሙበትና፣ እንደስራቸውም [ሐ]የሚፈረድባቸው ቀን ይመጣል።

፴፩ ሀ አልማ ፲፡ ፯–፲።
፴፩ ለ ሌለ. ፭፡ ፲–፲፩።
፴፩ ሐ ፩ ቆሮ. ፮፡ ፱–፲።
ለ ፩ ኔፊ ፲፭፡ ፴፫፤ አልማ ፴፡ ፳፯፤ ፫ ኔፊ ፳፯፡ ፲፱። ቅ.መ.መ. እግዚአብሔርን የሚጠላ።
ሐ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር መንግስት ወይም መንግስተ ሰማያት።
፴፩ ሀ ቁላ. ፩፡ ፲፯፤ ሞዛያ ፬፡ ፪።
ለ ኢሳ. ፱፡ ፯።
፴ ሀ ሮሜ ፲፩፡ ፳፯–፳፯።
ለ ቅ.መ.መ. አለም።
ሐ ዘፀአ. ፴፡ ፯–፲፤ ኢሳ. ፶፫፡ ፭፤ ፩ ዮሐ. ፪፡ ፪፤ ሞዛያ ፲፡ ፭፤ ፲፭፡ ፲፪፤ ት. እና ቃ. ፲፱፡ ፲፯–፲፱።
፴፩ ሀ አልማ ፲፪፡ ፲፮፤ ት. እና ቃ. ፹፯፡ ፴፫።
ለ ራዕ. ፳፡ ፲፪–፲፫፤ አልማ ፴፪፡ ፳፫።
ሐ ቅ.መ.መ. ፍርድ፡ የመጨረሻው።

፵፪ እንግዲህ፣ ጊዜያዊ ሞት ተብሎ የሚ
ጠራ ሞት አለ፤ እናም ሁሉም ከዚህ ከጊዜ
ያዊው ሞት ይነሱ ዘንድ፣ የክርስቶስ ሞት
የጊዜያዊ ሞትን [ሀ]እስር ይፈታል።

፵፫ መንፈስም ከስጋ ጋር ፍፁም በሆነ
ሁኔታ [ለ]በድጋሚ አንድ ይሆናል፣ እግርና
እጅ እናም መገጣጠሚያዎች ተገቢ በሆነ
ሁኔታ፣ እኛ አሁን ባለን አምሳል ይመ
ለሳሉ፤ እናም ልክ አሁን እንደምናውቅ
እያወቅንና፣ [ሐ]የጥፋታችን ሁሉ [መ]ትውስታ
ግልፅ እየሆነልን በእግዚአብሔር ፊት እን
ቀርባለን።

፵፬ እንግዲህ፣ ይህ ዳግሞ መመለስ ለሁ
ሉም፣ ለሽማግሌዎችና ለወጣቶች፣ ለታሰ
ሩና ነፃ ለሆኑትም፣ ለሴትና ለወንድ፣ ለኃ
ጢአተኞችና ለፃድቃን ይሆናል፤ እናም
አንዲትም የራስ ፀጉራቸውም እንኳን
አይጠፋም፤ ነገር ግን ሁሉም ነገር፣ ልክ
እንዳሁኑ፣ ወይም በሰውነት፣ በፍጹም
መልክ [ሀ]ይመለሳል፣ እናም [ለ]አንድ ዘለዓለ
ማዊ አምላክ በሆኑት በወልድ በክርስቶስና
በእግዚአብሔር [ሐ]አብ፣ እንዲሁም በመ
ንፈስ ቅዱስ የፍርድ ወንበር ፊት፣ መል
ካም ወይም ክፉዎች ቢሆኑ፣ እንደስራ
ቸው [መ]ሊፈረድባቸው መልስ ለመስጠት
ይመጣሉ።

፵፭ አሁን፣ እነሆ፣ ስለሚሞተው ሰው
ነታችን ሞት እናም ደግሞ ስለሚሞተው
ሰውነታችን [ሀ]ትንሳኤ ተናግሬሀለሁ። ይህ
የሚሞተው ሰውነት [ለ]ወደማይሞተው ሰው
ነት [ሐ]ይነሳል፣ ይህም ማለት ከሞት፣ እንዲ
ሁም ከመጀመሪያው ሞትም ወደ ህይወት፣
[መ]ከእንግዲህም ደግሞ እንዳይሞቱ ይነሳል
እልሀለሁ፤ መንፈሳቸው ከሰውነታቸው ጋር
አንድ ይሆናል፣ ከእንግዲህም አይለያይም፤
እንደዚህም አንድ የሆነው ሰውነትም [ሠ]መን
ፈሳዊና የማይሞት የማይበሰብስም ይሆናል።

፵፮ አሁን፣ አሙሌቅ እነዚህን ቃላት
በጨረሰ ጊዜ ህዝቡ በድጋሚ መገረም
ጀመረ፣ እናም ደግሞ ዚኤዝሮም መንቀጥ
ቀጥ ጀመረ። እናም የአሙሌቅ ቃል አበቃ፣
ወይንም የፃፍኩት ሁሉ ይህ ነው።

ምዕራፍ ፲፪

*አልማ ከዚኤዝሮም ጋር ተነጋገረ—የእ
ግዚአብሔር ሚስጥር ሊሰጥ የሚችለው
ለሚታመኑበት ብቻ ነው—ሰዎች በሀሳ
ባቸው፣ በእምነታቸው፣ በቃላቸውና በስ
ራቸው ይፈረድባቸዋል—ኃጢአተኞች
በመንፈሳዊ ሞት ይሰቃያሉ—ይህ ሞት
ያለበት ህይወት የሙከራ ጊዜ ነው—የቤዛ
ነት ዕቅድ ትንሳኤን እናም በእምነት የኃ
ጢያትን ስርየት ያመጣል—ንስሃ የሚ
ገቡ በአንድያ ልጅ አማካኝነት ምህረትን
የመቀበል መብት አላቸው። በ[ሠ]፪ ም.ዓ.
ገደማ።*

፩ አሁን አልማ የአሙሌቅ ቃል ዚኤዝሮ
ምን ዝም ማሰኘቱን ሲመለከት፣ አሙሌቅ
ዚኤዝሮም [ሀ]በመዋሸትና በማታለል ሊያ
ጠፋው ሲሞክር እንደያዘው ተመልክቷ
ልና፣ እናም ጥፋቱ [ለ]በማወቁ ምክንያት
መንቀጥቀጥ እንደጀመረ ስለተመለከተ፣
አፉን ከፍቶ ለእርሱ መናገርና፣ የአሙሌ
ቅን ቃላት ማረጋገጥ፣ እናም ከዚያን በላይ
የሆኑትን ነገሮች መግለጽ ወይም አሙሌ
ቅም ካደረገው በላይ ቅዱሳት መጻሕፍትን
መግለጽ ጀመረ።

፪ አሁን አልማ ለዚኤዝሮም የተናገረው
ቃላት በአካባቢው ላሉት ሰዎች ተሰምቶ

፵፪ *ሀ* አልማ ፲፪፡ ፲፯።
፵፫ *ሀ* ፪ ኔፊ ፱፡ ፲፫፣
አልማ ፵፡ ፷፫።
ለ ቅ.መ.መ. በደል።
ሐ ፪ ኔፊ ፱፡ ፲፡
ሞዛያ ፫፡ ፳፭፣
አልማ ፭፡ ፲፯።
፵፬ *ሀ* አልማ ፵፩፡ ፲፪–፲፭።
ለ ፫ ኔፊ ፲፭፡ ፳፯፣ ፴፯።
ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣
አምላክ።
ሐ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣
አምላክ—እግዚአብሔር
አብ።
መ ራዕ. ፳፡ ፲፪–፲፫።
፵፭ *ሀ* አልማ ፵፡ ፳፫፣
ት. እና ቃ. ፹፯፡ ፲፯።
ለ ቅ.መ.መ. የማይሞት፣
አለሟችነት።
ሐ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
መ ራዕ. ፳፩፡ ፬፣
ት. እና ቃ. ፯፫፡ ፵፱፣
፹፯፡ ፹፲፯።
ሠ ፩ ቆሮ. ፲፭፡ ፵፬።
፲፪ ፩ *ሀ* አልማ ፲፩፡ ፳–፴፯።
ለ ቅ.መ.መ. ህሊና።

ነበር፤ ህዝቡ ብዙ ነበሩና፣ እናም በዚህ መንገድ ተናገረ፤

፫ አሁን ዚኤዝሮም በሀሰተኝነትህና በተ ንኮል ተይዘሀል፣ አንተ ለሰዎች ብቻ ሳይ ሆን ለእግዚአብሔርም ዋሽተሀልና፤ እነ ሆም፣ እርሱ ሀሳብህን በሙሉ ያውቃል፣ እናም ያንተ *ሀሳብ በሙሉ በእርሱ መን ፈስ አማካኝነት ለእኛ እንድናውቀው እን ደሚሆን ትመለከታለህ፤

፬ እንግዲህ እኛን ተሳድበህ ለመጣል ህዝ ቡንም ለመዋሸትና ለማታለል በእኛ ላይ ያደረከው ዕቅድህ እጅግ የረቀቀ ዕቅድ እን ደሆነ እናውቃለን፣ እንደዲያብሎስም የረ ቀቀ ነው—

፭ አሁን ይህ *የጠላትህ ዕቅድ ነበር፣ እናም እርሱ ስልጣኑን በአንተ አሳይቷል። አሁን ለአንተ ያልኩትን ለሁሉም እንደ ምላቸው እንድታስታውሱ እፈልጋለሁ።

፮ እናም እነሆ ለሁላችሁም እላችኋለሁ ይህ የጠላት ወጥመድ ነው፣ ይህም ለእ ርሱ እንድትገዙ ለማድረግ ለምርኮ ባለው ስልጣኑ መሰረት፣ በሰንሰለቱም ይከባችሁ ዘንድ፣ በዘለአለማዊ ጥፋት *ሰንሰለት ይመ ታችሁም ዘንድ፣ ይህን ህዝብ ለመያዝ ያጠ መደው ነው።

፯ እንግዲህ አልማ እነዚህን ቃላት በተ ናገረ ጊዜ፣ ዚኤዝሮም እጅግ መንቀጥቀጥ ጀመረ፣ እርሱም በይበልጥ የእግዚአብሔ ርን ኃይል አምኗልና፤ እናም ደግሞ አል ማና አሙሌቅ ስለእርሱ እውቀት እንዳላ ቸው አመነ፣ የልቡን ሀሳብና መሻት እን ደሚያውቁ አምኗልና፤ በትንቢት መን ፈስ መሠረት ስለእነዚህ ነገሮች እንዲያ ውቁ ስልጣን ተሰጥቷቸው ነበርና።

፰ እናም ዚኤዝሮም ስለእግዚአብሔር መንግስት ይበልጥ ያውቅ ዘንድ በትጋት ይጠይቃቸው ጀመር። እናም ለአልማ እንዲህ አለው፥ አሙሌቅ ስለሙታን ትን ሳኤ፣ ሁሉም ከሞት ይነሳል፣ ፃድቅም ሆነ ኃጢአተኛ፣ እናም በስራቸው እንዲፈረድ ባቸው በእግዚአብሔር ፊት መጥተው ይቆ ማሉ ያለው ምን ማለቱ ነው?

፱ እናም አሁን አልማ እነዚህን ነገሮችን እንዲህ በማለት ማብራራት ጀመረ፣ ለብ ዙዎች *የእግዚአብሔርን ሚስጥር እንዲያ ውቁ ተሰጥቷቸዋል፤ ይሁን እንጂ ለሰዎች ልጆች ለእርሱ በሚሰጡት ትኩረትና ትጋት መሰረት እንዲሰጣቸው ከሚፈቅደው የቃሉ ^ክፍል በስተቀር እንዳይካፈሉ ጥብቅ ትዕ ዛዝ ውስጥ ገብተው ነበር።

፲ እናም ስለዚህ ልቡን *የሚያጠጥር፣ እርሱም ከቃሉ ^ትንሹን ክፍል ይቀበላል፤ እናም ልቡንም *ሐየማያጠጥር ለእርሱ ሁሉ ንም በሙላት የእግዚአብሔርን ሚስጥር እስከሚያውቅ ድረስ ከቃሉ ትልቅ ክፍል ᵐይሰጠዋል።

፲፩ እናም ልባቸውን የሚያጠጥሩ ሚስ ጥሩን በተመለከተ *ምንም እስከማያውቁ ድረስ የቃሉ ትንሽ ^ክፍል ይሰጣቸዋል፤ እና ከእዚያም በዲያብሎስ ምርኮ ይወሰዳ ሉና፣ እስከሚጠፉም በፈቃዱ ይመራሉ። እናም *ሐየሲኦል ᵐሰንሰለትም ማለት ይህ ነው።

፲፪ እናም አሙሌቅ *ሞትን በተመለ ከተ፣ ከሚሞት ሰውነት ወደ ማይሞት ሰው ነት ስለመነሳት፣ እናም በእግዚአብሔርም የፍርድ ወንበር ፊት እንደስራችን ^ሊፈረ ድብን ስለመቅረባችን በግልፅ ተናግሯል።

፫ *ሀ* ያዕቆ. ፪፡፭፤ አልማ ፲፡፲፯፤ ት.እና ቃ. ፮፡፲፯።
፭ *ሀ* ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
፮ *ሀ* አልማ ፭፡፲–፲፤
፱ *ሀ* አልማ ፳፯፡፳፪። ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ሚስጥሮች።
ለ ዮሐ. ፲፯፡፲፪፤ አልማ ፳፱፡፳፤
፫ ኔፊ ፳፯፡፳–፲፩፤ ኤተር ፬፡፲፯።
፲ *ሀ* ፪ ኔፊ ፳፰፡፳፯፤ ኤተር ፬፡፳።
ለ ት.እና ቃ. ፶፫፡፴፱። *ሐ* ቅ.መ.መ. ትሁት፣ ትሕትና።
መ ፪ ኔፊ ፳፰፡፴፣ ት.እና ቃ. ፶፡፳፰።
፲፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. ክህደት።
ለ ማቴ. ፳፭፡፭፤ ፳፱።
ሐ ምሳ. ፱፡፲፰፤ ፪ ኔፊ ፪፡፳፱። ቅ.መ.መ. ሲያል።
መ ዮሐ. ፳፡፴፣ ፪ ኔፊ ፳፰፡፲፤
፲፪ *ሀ* አልማ ፲፩፡፶፩–፶፭።
ለ ቅ.መ.መ. ፍርድ፣ የመጨረሻው።

፲፫ ከዚያም ልባችን ከጠጠረ፣ አዎን፣ በውስጣችን እስካማይገኝ ድረስ በቃሉ ልባችንን ካጠጠርን፣ ከዚያም በኋላ ጉዳያችን የከፋ ይሆናል፣ እንኮነናለን።

፲፬ [ሀ]ቃላቶቻችን ይፈርዱብናል፣ አዎን ስራዎቻችን ሁሉ ይፈርዱብናል፤ እንከን የሌለብንም በመሆን አንገኝም፣ እናም ሀሳባችንም ደግሞ ይፈርድብናል፤ እናም በዚህ አስከፊ ሁኔታ ወደ አምላካችን ለመመልከት አንደፍርም፤ እናም አለቶቹንና [ለ]ተራራዎቹን ከእርሱ ፊት [ሐ]እንዲደብቁን በላያችን ላይ እንዲወድቁ ብናዛቸው እጅግ እንደሰታለን።

፲፭ ነገር ግን ይህ ሊሆን አይችልም፣ ወደ ፊቱ መምጣትና በክብሩ እናም በስልጣኑና በኃይሉ፣ በክብሩና በአለቅነቱ መቆም፣ እናም በዘለዓለማዊ [ሀ]እፍረታችን [ለ]ፍርዱ በሙሉ ትክክል እንደሆነ፣ እርሱም በስራው ሁሉ ትክክል እንደሆነና፣ ለሰው ልጆች መሃሪ እንደሆነ፣ እንዲሁም በስሙ የሚያምኑትንና ለንስሃ የሚሆን ፍሬን የሚያስገኙትን ማንኛውንም ሰው ለማዳን ስልጣን እንዳለው እናረጋግጣለን።

፲፮ እናም አሁን እነሆ፣ እንዲህ እላችኋለሁ [ሀ]ሞት፣ እንዲሁም መንፈሳዊው ሞት የሆነው ሁለተኛው ሞት ይመጣል፣ ከእዚያም በኃጢአቱ [ለ]ጊዜያዊ ሞትን [ሐ]የሚሞት መንፈሳዊ የሆነውን ሞትን ይሞትበታል፤ አዎን፣ ለፅድቅም በሆነ ነገር ሁሉ ይሞታል።

፲፯ ቅጣታቸው እንደ [ሀ]እሳት ባህርና ዲን፣ ነበልባሉም ከዘለዓለም እስከዘለአለም ወደ ሰማይ እንደሚወጣው የሚሆንበት ጊዜም ይህ ነው፤ እና ያም በሰይጣን ኃይልና ምርኮ መሰረት፣ እነርሱን እንደፈቃዱ ተገዝ በማድረግ፣ በዘለዓለማዊው ጥፋት የሚታሰሩበት ጊዜ ነው።

፲፰ ከዚያም፣ እላችኋለሁ፣ እነርሱም [ሀ]ቤዛነት እንዳልተፈፀመ ሆነው ይቆያሉ፣ በእግዚአብሔር ፍርድ መሰረት ሊድኑ አይችሉም፤ እናም [ለ]መሞት አይችሉም ምክንያቱም ከእንግዲህ መበስበስ አይኖርምና።

፲፱ እንግዲህ እንዲህ ሆነ አልማ ይህንን ንግግር እንደጨረሰ፣ ህዝቡ ይበልጥ መገረም ጀመረ፤

፳ ነገር ግን አንቲዮና የሚባል ሰው ነበር፣ በእነርሱም መካከል ዋና ገዢ የነበረው መጣና እንዲህ አለው፥ ሰው ከሞት ይነሳል እናም ከሙታን [ሀ]ወደማይሞተውም ይለወጣል፣ ነፍሱም በጭራሽ አይሞትም ብለህ የተናገርከው ይህ ምንድን ነው?

፳፩ የመጀመሪያ ቤተሰቦቻችን እንዳይገቡና ከህይወት ዛፍ እንዳይወስዱ እናም ለዘለአለም እንዳይኖሩ እግዚአብሔር [ሀ]ኪሩቤልንና የነበልባሉን ሰይፍ [ለ]በዔድን ገነት በስተምስራቅ አስቀምጧል በማለት ቅዱሳን መፃህፍትስ የተናገሩት ምን ማለት ነው? እናም ለዘለአለም እንዲኖሩ ምንም እድል እንዳልነበረ እንመለከታለን።

፳፪ አሁን አልማ እንዲህ አለው፥ እኔ እንድገልፀው የነበረው ነገር ይህ ነው። አሁን አዳም በእግዚአብሔር ቃል መሰረት የተከለከለውን [ሀ]ፍሬ በመመገቡ [ለ]መውደቁን ተመልክተናል፤ እናም በመውደቁ የሰው ዘር በሙሉ [ሐ]የሚጠፋና የሚወድቅ እንደ ሆነም በዚህ እናያለን።

፲፩ ሀ ማቴ. ፲፪፡፴፮፤ ያዕ. ፫፡፮፤ ሞዛያ ፬፡፳፱–፴።
ለ ሆሴ. ፣ ፡ ፤ ፪ ኔፊ ፳፯፡፭።
ሐ ኢዮብ ፴፬፡፳፪፤ ፪ ኔፊ ፲፪፡፣ ፲።
፲፭ ሀ ሞዛያ ፫፡፳፭።
ለ ፪ ጴጥ. ፪፡፱። ቅ.መ.መ. ፍትህ።
፲፮ ሀ ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ሞት።

ለ አልማ ፲፭፡፶–፶፭።
ሐ ፩ ኔፊ ፲፭፡፴፣ አልማ ፶፡፳፯።
፲፯ ሀ ራዕ. ፲፱፡፳፣ ፳፡፣ ሞዛያ ፫፡፳፯።
፲፰ ሀ አልማ ፲፭፡፴፯።
ለ ራዕ. ፳፭፡፱፤ አልማ ፲፭፡፶፣ ት. እና ቃ. ፳፫፡፶፱።
፳ ሀ ቅ.መ.መ. የማይሞት፣ አለሟችነት።

፳፩ ሀ ዘፍጥ. ፫፡፳፬፤ አልማ ፶፪፡፪፣ ሙሴ ፬፡፴፭። ቅ.መ.መ. ኪሩቤል።
ለ ቅ.መ.መ. ዔድን።
፳፪ ሀ ዘፍጥ. ፫፡፣ ፤ ፪ ኔፊ ፪፡፲፭–፲፱፣ ሞዛያ ፫፡፳፯።
ለ ቅ.መ.መ. የአዳም እና የሔዋን ውድቀት።
ሐ ሞዛያ ፲፣ ፡–፲።

፳፫ እናም አሁን እነሆ እላችኋለሁ፣ በዚያን ጊዜ ለአዳም ከህይወት ዛፍ ፍሬ [ሀ]መመገብ የሚቻለው ቢሆን ኖሮ፣ ሞት አይኖርም ነበር፣ እናም ቃሉም ዋጋ የሌለው ይሆን ነበር፣ ይህንን [ለ]በበላችሁ ጊዜ በእርግጥ ትሞታላችሁ ብሎም ተናግሮ ነበርና፣ እግዚአብሔርንም ውሸታም ያደርገው ነበር።

፳፬ እናም ሞት፣ አዎን፣ በአሙሌቅ የተነገረው ጊዜያዊ [ሀ]ሞት በሰው ዘር ላይ መምጣቱን እንመለከታለን፤ ይሁን እንጂ [ለ]የሰው ልጅ ንስሃ ይገባ ዘንድ የተሰጠው ጊዜ ነበር፣ ስለሆነም ይህ ህይወት የሙከራ ጊዜ፣ እግዚአብሔርን ለመገናኘት [ሐ]የመዘጋጃ ጊዜ፣ ከትንሣኤ በኋላ ለሚሆነው እኛ ለተነገርነው መጨረሻ ለሌለው ሁኔታ መዘጋጃ ጊዜ ይሆናል።

፳፭ አሁን፣ ከዓለም መፈጠር ጀምሮ በነበረው [ሀ]የቤዛነት ዕቅድ ባይሆን ኖሮ፣ የሙታን [ለ]ትንሳኤ ሊሆን ባልቻለም ነበር፣ ነገር ግን የተነገረውን የሙታን ትንሳኤ የሚያመጣ የቤዛነት ዕቅድም ተዘጋጅቶ ነበር።

፳፮ እናም አሁን እነሆ፣ የመጀመሪያ ወላጆቻችን ሄደውና [ሀ]የህይወት ዛፍን መመገብ ቢችሉ ኖሮ የሚዘጋጁበት ሁኔታ ሳይኖራቸው ለዘለዓለም ደስታ የሌላቸው በሆኑ ነበር፤ እናም [ለ]የቤዛነት ዕቅድም በከሸፈና የእግዚአብሔር ቃል ውጤት ሳይኖረው ዋጋ የሌለው በሆነም ነበር።

፳፯ ነገር ግን እነሆ፣ እንዲህ አልነበረም፤ ነገር ግን ሰዎች መሞት እንዳለባቸው [ሀ]ተመድቦ ነበር፣ እናም ከሞት በኋላ፣ [ለ]ለፍርድ፣ እንዲሁም እኛ የተናገርነው ዓይነት የመጨረሻ ለሆነ ፍርድ መምጣት አለባቸው።

፳፰ እናም እግዚአብሔር እነዚህ ነገሮች ለሰው ልጆች መምጣት እንዳለባቸው ከመደበ በኋላ፣ እነሆ፣ ሰዎችም የተወሰነላቸውን ነገር በተመለከተ ማወቅ እንደነበረባቸው ተመለከተ፤

፳፱ ስለዚህ ከእነርሱ ጋር እንዲነጋገሩ፣ ሰዎችንም ክብሩን እንዲመለከቱ ያደረገ [ሀ]መላዕክት ላከ።

፴ እናም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ስሙን መጥራት ጀመሩ፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር [ሀ]ተነጋገረ፤ እናም ከዓለም መፈጠር ጀምሮ ተዘጋጅቶ የነበረውን [ለ]የቤዛነት ዕቅድም እንዲያውቁ አደረገ፣ እናም ይህን እንዲያውቁ ያደረገው በእምነታቸውና በንስሃቸው እንዲሁም በቅዱሱ ስራቸው [ሐ]መሰረት ነው።

፴፩ ስለዚህ፣ ጊዜያዊ የነበሩትንም ነገሮች በተመለከተ [ሀ]የመጀመሪያዎቹን ትዕዛዛት በመተላለፋቸው፣ እናም እንደ አማልክት መልካሙን ከክፉ [ለ]እንዲያውቁ በመሆናቸው፣ እራሳቸውን [ሐ]ለመስራት በሚችሉበት ሁኔታ፣ ወይም እንደፍላጎታቸውና እንደደስታቸው፣ ክፉ ወይንም መጥፎውን ለማድረግ በሚችሉበት ቦታ እያሉ፣ ለሰዎች [መ]ትዕዛዛትን ሰጠ፣

፴፪ ስለዚህ እግዚአብሔር ስለቤዛነት ዕቅድ [ሀ]እንዲያውቁ ካደረገ በኋላ፣ ቅጣቱ ሁለተኛ [ለ]ሞት፣ ይህም ጻድቃንን በሚመለከት ነገሮች የዘለአለም ሞት በሆነው መጥፎ እንዳይሰሩ ትዕዛዛትን ሰጣቸው፤ ለእንደነዚህ ዓይነቱ የቤዛነት ዕቅድ ኃይል ሊኖረው

፳፫ ሀ አልማ ፵፪፥ ፪–፱።
ለ ዘፍጥ. ፪፥ ፲፯።
፳፬ ሀ ቅ.መ.መ. ስጋዊ ሞት።
ለ ፪ ኔፊ ፪፥ ፳፩፤
ሙሴ ፭፥ ፰–፲፪።
ሐ አልማ ፴፬፥ ፴፪–፴፭።
፳፭ ሀ ቅ.መ.መ. የቤዛነት ዕቅድ።
ለ ፪ ኔፊ ፪፥ ፰፤
አልማ ፯፥ ፲፪፤ ፵፪፥ ፳፫።
፳፮ ሀ ዘፍጥ. ፪፥ ፱፤
፩ ኔፊ ፲፭፥ ፴፮፤
አልማ ፴፪፥ ፵።
ለ አልማ ፴፬፥ ፰–፲፮፤
፵፪፥ ፮–፳፰፤
ሙሴ ፮፥ ፶፱–፷፪።
፳፯ ሀ ኢዮብ ፯፥ ፩፤
ዕብ. ፱፥ ፳፯፤
ት. እና ቃ. ፵፪፥ ፵፰።
ለ ቅ.መ.መ. ፍርድ፣
የመጨረሻው።
፳፱ ሀ ሞሮኒ ፯፥ ፳፭፣ ፴፩፤
ት. እና ቃ. ፳፱፥ ፵፪።
፴ ሀ ሙሴ ፭፥ ፬–፭፤ ፮፥ ፶፩።
ለ ቅ.መ.መ. የቤዛነት ዕቅድ።
ሐ ሞዛያ ፲፰፥ ፲፫፤
አልማ ፲፫፥ ፫፣ ፭፣ ፯–፰።
፴፩ ሀ ዘፍጥ. ፪፥ ፲፮–፲፯፤
፪ ኔፊ ፪፥ ፲፰–፲፱።
ለ ዘፍጥ. ፫፥ ፳፪–፳፫፤
ሙሴ ፬፥ ፲፩።
ሐ ፪ ኔፊ ፪፥ ፲፮።
ቅ.መ.መ. ነጻ ምርጫ።
መ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር
ትእዛዛት።
፴፪ ሀ ሙሴ ፭፥ ፬–፱።
ለ ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ሞት።

አይችልምና፣ ምክንያቱም በቸሩ አምላክ ኃያልነት ᎐የፍርድ ስራዎች ሊጠፉ አይ ቻላቸውምና።

፴፫ ነገር ግን እግዚአብሔር በልጁ ስም ሰዎችን ጠራ፣ (ይህም የተዘረጋው የቤዛነት ዕቅድ ነው) እንዲህም አለ፥ ንስሃ የምት ገቡ፣ እናም ልባችሁን የማታጠጥሩ ከሆነ፣ ከዚያም በአንድያ ልጄ አማካኝነት ምህረ ትን አደርግላችኋለሁ።

፴፬ ስለዚህ፣ ማንኛውም ንስሃ የሚገቡ እናም ልባቸውን የማያጠጥሩ ለኃጢአ ታቸው ᐧስርየት በአንድያ ልጄ አማካኝነት ᐩምህረት ይገባቸዋል፤ እና እነዚህም ᎐በእ ረፍቴ ይገባሉ።

፴፭ እናም ማንኛውም ልባቸውን የሚያ ጠጥሩና ክፋትን የሚያደርጉ፣ እነሆ፣ በእ ረፍቴ እንደማይገቡ በቁጣዬ እምላለሁ።

፴፮ እናም አሁን፣ ወንድሞቼ፣ እነሆ እን ዲህ እላችኋለሁ፣ ልባችሁን የምታጠጥሩ ከሆነ በጌታ እረፍት ውስጥ አትገቡም፤ ስለ ዚህ መተላለፋችሁ ቁጣውን በእናንተ ላይ ᐧበመጀመሪያ ጥፋት እንዳደረገው እንዲ ልክ ያነሳሳዋል፣ አዎን፣ ለዘለዓለም ለነፍ ሳችሁ ᐩጥፋት እንደቃሉ የመጨረሻ ቁጣ ውን እንደ መጀመሪያው ይልካል፣ ስለዚህ በቃሉ መሰረት በመጀመሪያው ሞት ልክ እንደ መጨረሻው ይሆንባችኋል።

፴፯ እናም አሁን፣ ወንድሞቼ፣ እነዚህን ነገሮች ስለምናውቅና፣ እውነት በመሆና ቸው፣ ንስሃ እንግባና ልባችንን አናጠጥር፣ እግዚአብሔር ለእኛ በሰጠው በሁለተኛው ትዕዛዝ ቁጣውን በእኛ እንዲያደርግም ᐧአን ቀስቅሰው፤ ነገር ግን በቃሉ መሰረት ወደተ ዘጋጀው ᐩየእግዚአብሔር እረፍት እንግባ።

ምዕራፍ ፲ ፫

ሰዎች በታላቁ እምነታቸውና በመልካም ስራዎቻቸው ሊቀ ካህን ተብለው ይጠ ራሉ—ትዕዛዛቱን ያስተምሩ—በፅድቅ ይቀደሳሉ እናም ወደጌታ እረፍት ይገ ባሉ—መልከ ጼዴቅ ከእነዚህ ውስጥ አንዱ ነበር—መላዕክት የምስራች ወሬውን በም ድሪቱ ያውጃሉ—የክርስቶስን በእርግጥ መምጣቱን ያውጃሉ። በ፹፪ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም በድጋሚ፣ ወንድሞቼ፣ ጌታ እግ ዚአብሔር እነዚህን ትዕዛዛት ለልጆቹ ወደ ሰጠበት ጊዜ አዕምሮአችሁን እጠቁማለሁ፤ እናም ጌታ እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች ለህዝብ እንዲያስተምሩ የልጁ ቅዱስ ሥር ዓት መሰረት በሆነው በቅዱስ ሥርዓቱ ካህ ናትን ᐧመሾሙን እንድታስታውሱ እፈል ጋለሁ።

፪ እናም ካህናቱ የተሾሙት ᐧበልጁ ሥር ዓት መሠረት ነበር፣ ᐩበስርዓቱም ህዝቡ ወልድን ለቤዛቸው በምን ሁኔታ መመል ከት እንዳለባቸው ያውቁ ዘንድ ነው።

፫ እናም የተሾሙበት ሥርዓት በዚህ ሁኔታ ነበር—እናም ከዓለም ᐧመፈጠር ጀምሮ በእግዚአብሔር ᐩበቀደመው እው ቀት መሰረት በእምነታቸውና በመልካም ስራዎቻቸው ᐸተጠርተዋል፣ ᐧተዘጋጅተ ዋልም፤ በመጀመሪያ ደረጃ መጥፎና ጥሩ ውን ᐧእንዲመርጡ ተትተዋል፤ ስለዚህ መልካሙን በመምረጣቸውና ታላቅ ᐹእም ነትን በመለማመዳቸው በቅዱሱ አጠራር፣ አዎን፣ ለእንደእነዚህ አይነት ሰዎች በቤዛ ነት ዝግጅት ጋር፣ እናም መሰረት፣ በተዘ ጋጀው ቅዱስ ጥሪ ᐪተጠርተዋል።

፴፪ሐ ሞዛያ ፲ ፭ ፡ ፳ ፯ ፤
አልማ ፴ ፱ ፡ ፲ ፭–፲ ፮ ፤
፵ ፪ ፡ ፲ ፭ ።
፴ ፱ ሀ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ስርየት ።
ለ ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት ።
ሐ ቅ.መ.መ. እረፍት ።
፴ ፯ ሀ ያዕቆ. ፩ ፡ ፯–፰ ፤
አልማ ፵ ፪ ፡ ፮ ፣ ፱ ፣ ፲ ፱ ።
ለ ቅ.መ.መ. ኩነኔ ።
፴ ፯ ሀ ፩ ኔፊ ፲ ፯ ፡ ፴ ፣
ያዕቆ. ፩ ፡ ፰ ፤
ሔለ. ፯ ፡ ፲ ፰ ።
ለ አልማ ፲ ፫ ፡ ፮–፱ ።
፲ ፫ ፩ ሀ አብር. ፪ ፡ ፱ ፣ ፲ ፩ ።
፪ ሀ ት. እና ቃ. ፲ ፯ ፡ ፪–፭ ።
ለ አልማ ፲ ፫ ፡ ፲ ፮ ።
፫ ሀ አልማ ፲ ፪ ፡ ፳ ፭ ፣ ፴ ።
ቅ.መ.መ. ቅድመ ምድራዊ ህይወት ።
ለ ት. እና ቃ. ፴ ፳ ፡ ፪ ።
ሐ ት. እና ቃ. ፲ ፳ ፯ ፡ ፪ ።
ቅ.መ.መ. መመረጥ፣ ቀድሞ መመረጥ ።
መ ት. እና ቃ. ፲ ፴ ፣ ፶ ፭–፶ ፮ ።
ሠ ቅ.መ.መ. ነጻ ምርጫ ።
ረ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን ።
ሰ ቅ.መ.መ. ክህነት፣ ጥሪ፣ በእግዚአብሔር መጠራት፣ የተጠራበት ።

፬ እናም በእምነታቸው የተነሳ ለዚህ ቅዱሱ ጥሪ እንደዚህም ᵅተጠርተዋል፣ ይህ ሆኖ ሳለ፣ ሌሎች በልባቸው ጠጣርነትና በአዕምሮአቸው መታወር የእግዚአብሔርን መንፈስ አይቀበሉ፣ በሌላ መልኩ፣ በዚህ ባይሆን ኖሮ እንደወንድሞቻቸው ታላቅ ᵇመብት ይኖራቸው ነበር።

፭ በአጠቃላይ በመጀመሪያ ደረጃ እነርሱ ከወንድሞቻቸው ጋር ᵅአንድ ዓይነት አቋም ነበራቸው፣ ይህ ቅዱሱ ጥሪም ከዓለም መፈጠር ጀምሮ ልባቸውን ላላጠጠሩት ተዘጋጅቷል፣ የተዘጋጀውም በአንድያ ልጁ የኃጢያት ክፍያ አማካኝነት በኩል እናውስጥ ነበር—

፮ እናም በቅዱሱ ጥሪው እንዲህ በመጠራትና፣ ወደ ᵅእረፍቱም ይገቡ ዘንድ ለሰው ልጆች ትዕዛዛቱን ለማስተማር በእግዚአብሔር ቅዱሱ ስርዓት መሠረት ወደ ታላቁ ክህነት ተሹመዋል—

፯ ይህም ታላቁ ክህነት ከአለም መፈጠር ጀምሮ ከነበረው ከወልድ ሥርዓት መሰረት ነው፤ ወይም በሌላ አነጋገር፣ ᵅመጀመሪያም ቀናት ሆነ ፍፃሜ አመታት የሌለው፤ ለሁሉም ነገር ᵇበቀደመው እውቀቱ መሰረት ከዘለዓለም እስከዘለዓለም የተዘጋጀ ነው—

፰ አሁን በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ᵅተሹመዋል—በቅዱሱ ጥሪም ተጠርተውና፣ በቅዱሱ ስርዓት ተሹመው፣ ጥሪውና፣ ሹመቱ፣ እና ታላቁ ክህነት መጀመሪያና መጨረሻ የሌለውን የቅዱሱን ስርዓት ታላቅ ክህነት ተቀብለዋል—

፱ መጀመሪያ ቀናት ሆነ መጨረሻ አመታት በሌለው፣ ᵅበፀጋ፣ ፍትህና እውነት በተሞላው በአብ አንድያ ልጅ፣ እንደ ወልድ ስርዓት መሠረት ለዘለአለም ᵇሊቀ ካህናት እንደዚህ ሆኑ። እናም እንደዚህ ነው። አሜን።

፲ እንግዲህ፣ ስለቅዱሱ ስርዓትም ሆነ ስለዚህ ᵅታላቁ ክህነት በተመለከተ በተናገርኩ ጊዜ፣ ብዙዎች የተሾሙና የአምላክ ሊቀ ካህን የሆኑ ነበሩ፤ እናም ይህም በታላቁ እምነታቸውና ᵇንስሃ በመግባታቸው፣ እናም በእግዚአብሔር ፊት ባላቸው ብፁዕነት ንስሃ ለመግባትና ከመጥፋትም ፅድቅን ለመስራት በመምረጣቸው ምክንያት ነው፤

፲፩ ስለዚህ በዚህ ቅዱስ ስርዓት ተጠርተው ነበር፣ ᵅተቀድሰውም ነበር፣ እናም በበጉ ደም ᵇልብሳቸው እስከሚነጣ ታጥበው ነበር።

፲፪ እንግዲህ እነርሱ ᵅበቅዱስ መንፈስ ᵇከተቀደሱ በኋላ፣ ልብሳቸው ከነጣ፣ በአምላክ ፊት ᶜንፁህና እንከን የለሽ ከሆኑ፣ ᵈኃጢያትን ᵉከመጥላት በቀር ሊመለከቱትም አልቻሉም፣ እናም ንፁህ የሆኑና ወደ ጌታ አምላካቸው እረፍት የገቡ ብዙዎች፣ እጅግ ብዙዎች፣ ነበሩ።

፲፫ እናም አሁን፣ ወንድሞቼ፣ በእግዚአብሔር ፊት ራሳችሁን ትሁት እንድታደርጉ፣ እናም ለንስሃም ብቁ የሆነ ᵅፍሬን እንድታመጡ፣ እናንተም በእረፍቱ ትገቡ ዘንድ እፈልጋለሁ።

፲፬ አዎን፣ እኔ በተናገርኩት ተመሳሰይ ሥርዓት መሠረት ሊቀ ካህን የነበረው፤ ታላቁ ክህነትን ለዘለአለም እንደተቀበለው ᵅመልከ ፄዴቅ ጊዜ እንደነበሩት ሰዎች ራሳችሁን ትሁት አድርጉ።

፬ ሀ ኤተር ፲፪፥፲።
ለ ፩ ኔፊ ፲፯፥፴፪–፴፭።
፭ ሀ ፪ ኔፊ ፳፮፥፳፰።
፮ ሀ አልማ ፲፪፥፴፯፤ ፲፮፥፲፯።
ቅ.መ.መ. እረፍት።
፯ ሀ ዕብ. ፯፥፫።
ለ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ።
፰ ሀ ት. እና ቃ. ፹፬፥፴፫–፵፪።
ቅ.መ.መ. የመልከ ጼዴቅ ክህነት።
፱ ሀ ፪ ኔፊ ፪፥፮።
ቅ.መ.መ. ጸጋ።
ለ ቅ.መ.መ. ሊቀ ካህን።
፲ ሀ ት. እና ቃ. ፹፬፥፲፰–፳፪።
ለ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣ ንስሀ መግባት።
፲፩ ሀ ሙሴ ፮፥፶፱–፷።
ለ ፩ ኔፊ ፲፪፥፲፤
አልማ ፭፥፳፩–፳፯፤
፫ ኔፊ ፳፯፥፲፱–፳።
፲፪ ሀ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
ለ ሮሜ ፰፥፩–፱።
ቅ.መ.መ. ቅድስና።
ሐ ቅ.መ.መ. ንጹህ፣ ንጹህነት።
መ ሞዛያ ፭፥፪፤
አልማ ፲፱፥፴፫።
ሠ ምሳ. ፰፥፲፫፤
አልማ ፴፯፥፳፱።
፲፫ ሀ ሉቃ. ፫፥፰።
፲፬ ሀ ጆ.ስ.ት. ዘፍጥ. ፲፬፥፳፭–፵ (ተጨማሪ)።
ት. እና ቃ. ፹፬፥፲፬።
ቅ.መ.መ. መልከ ጼዴቅ።

፲፭ እናም ለዚህ መልከ ጼዴቅ ነበር ᵐአብ ርሃም ᵃአስራት የከፈለው፣ አዎን፣ አባታ ችን አብርሃም ከነበረው ሀብት እንኳን አንድ አስረኛውን አስራት ከፍሏል።

፲፮ አሁን ይህ የሥርዓቱም ሁኔታ ሆኖ ወይንም ይህ የእርሱ ᵐሥርዓት ሆኖ፣ በዚህ ህዝብ ወደ እግዚአብሔር ልጅ ይመለ ከቱ ዘንድ እነዚህ ስርዓቶች ᵃበዚህ ሁኔታ ነበር የተሰጡት፣ እና ይህም ለኃጢአታ ቸው ሥርየትም ወደፊት ወደእርሱ ይመ ለከቱት ዘንድ፣ ወደጌታም ዕረፍት ይገቡ በት ዘንድ ነው።

፲፯ እንግዲህ ይህ መልከ ጼዴቅ በሳሌም ምድር ንጉስ ነበር፣ እናም ህዝቡም በክ ፋትና በእርኩሰታቸው የጠነከሩ ነበሩ፤ አዎን፣ ሁሉም የተሳሳቱ ነበሩ፤ በሁሉም ዓይነት ክፋትም ተሞልተው ነበር።

፲፰ ነገር ግን መልከ ጼዴቅ ታላቅ እምነትን ተለማመደ፣ የታላቅ ክህነት ሀላፊነትን በእ ግዚአብሔር ᵐቅዱሱ ስርዓት መሰረት በመ ቀበል ለህዝቡ ንስሃን ሰበከ። እናም እነሆ፣ እነርሱ ንስሃ ገቡ፤ በዘመኑም መልከ ጼዴቅ ሰላምን በምድር ውስጥ መሰረተ፤ ስለዚህ የሳሌም ንጉስ በመሆኑ የሰላም አለቃ ተብሎ ተጠርቷል፤ እናም በአባቱም በታች ነገሰ።

፲፱ አሁን፣ ከፊቱ ᵐብዙዎች ነበሩ፣ እናም ደግሞ ከእርሱ በኋላ ደግሞ ብዙዎች ነበሩ፣ ነገር ግን ᵃማንም ታላቅ አልነበረም፤ ስለ ዚህ፣ በይበልጥ ስለእርሱ በልዩ ጠቅሰዋል።

፳ አሁን ይህን ጉዳይ እንደገና መናገር አያስፈልገኝም፣ የተናገርኩት ይበቃል። እነሆ፣ ᵐቅዱሳት መጻሕፍት ከፊታችሁ ይገኛሉ፤ ᵃየምታጣምሙት ከሆነ ለጥፋ ታችሁ ይሆናል።

፳፩ እናም አሁን እንዲህ ሆነ አልማ እነ ዚህን ቃላት ለእነርሱ በተናገረ ጊዜ፣ እጁን ዘርግቶ በኃይል እንዲህ በማለት ይጮህ ነበር፣ አሁን ᵐየንስሃ ጊዜ ነው፣ የደህንነት ቀን ቀርባለችና፤

፳፪ አዎን፣ እናም የጌታ ድምፅ፣ በመል አኩ ᵐአንደበት፣ ለሀገር ሁሉ አውጇል፣ አዎን፣ በታላቅ ደስታ የምስራች ወሬ ይኖ ራቸው ዘንድ ያውጀዋል፤ አዎን፣ እናም በህዝቡ መካከል፣ አዎን፣ በምድር ፊት እስከዳርቻ ለተበተኑትም እንኳን፣ እነዚ ህን የምስራች እንዲሰሙ ያደርጋል፤ ስለ ዚህ እነዚህ ወደእኛ መጥተዋል።

፳፫ እናም እኛ እንድንረዳቸው ዘንድ፣ እንዳንሳሳት ዘንድ፣ ᵐበግልፅ አባባል እንድ ናውቃቸው ተደርገዋል፤ እናም ይህም የሆ ነው በባዕድ ምድር ᵃበመዘዋወራችን ነው፤ ስለዚህ፣ እኛ እነዚህን የምስራች ወሬዎች በወይን አትክልት ቦታዎቻችን ሁሉ ስለ ታወጁልን በይበልጥ ሞገስን አግኝተናል።

፳፬ እነሆም፣ ᵐመላዕክት በዚህ ጊዜ በም ድራችን ላይ ለብዙዎች እያወጁ ናቸው፤ እናም የዚህም ዓላማ በክብሩ ለሚመጣበት ጊዜ የሰው ልጆችን ልብ ለማዘጋጀት ነው።

፳፭ እናም አሁን ስለእርሱ መምጣት በመ ላዕክት አንደበት የሚነገሩትን አስደሳች ዜና ለማዳመጥ ብቻ እየጠበቅን ነን፤ ጊዜው እየ መጣ ነው፣ እንዴት እንደፈጠነ ᵐአናው ቅም። በእኔ ቀናት እንዲሆን ዘንድ እግዚ አብሔር ይፍቀደው፤ ነገር ግን በፍጥነት ወይም ዘግይቶ ቢሆን ይሁን፣ በእዚህም እደሰታለሁ።

፳፮ እናም ይህ በመልአኩ አንደበት፣ በሚመጣበት ጊዜ፣ እርሱን በተመለከተ

፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. አብርሐም።
ለ ዘፍጥ. ፲፬፡ ፲፰–፳፣ ሚል. ፫፡ ፰–፲። ቅ.መ.መ. አስራት፣ አስራት መክፈል።
፲፮ ሀ ቅ.መ.መ. ስነስርዓቶች።
ለ ቅ.መ.መ. ምሳሌዎች።
፲፰ ሀ ቅ.መ.መ. የመልከ ጼዴቅ ክህነት።
፲፱ ሀ ሐሌ. ፰፡ ፲፰፣ ት. እና ቃ. ፹፬፡ ፯–፲፯፣ ፻፯፡ ፵–፶፭።
ለ ት. እና ቃ. ፻፯፡ ፭–፱።
፳ ሀ ቅ.መ.መ. ቅዱሳት መጻህፍት።
ለ ፪ ጴጥ. ፫፡ ፲፯፣ አልማ ፵፭፡ ፩።
፳፩ ሀ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣ ንስሀ መግባት።
፳፪ ሀ አልማ ፲፡ ፳።
፳፫ ሀ ፪ ኔፊ ፳፭፡ ፯–፳፣ ፴፭፡ ፫፣ ፴፪፡ ፯፣ ያዕቆ. ፱፡ ፲፫፣ ኤተር ፲፪፡ ፴፱።
ለ ያዕቆ. ፯፡ ፳፯።
፳፬ ሀ አልማ ፲፡ ፲፣ ፴፱፡ ፲፱።
፳፭ ሀ ፩ ኔፊ ፲፡ ፱፣ ፫፡ ፲፫።
፳፯ እናም እንዲህ ሆነ ንጉሱ በምድሪቱ ሁሉ ባሉት ሰዎች መካከል፣ በዙሪያውም ባለው ክልል በባህሩም ዳርቻ፣ በምስራቅና በስተምዕራብ፣ ከዛራሔምላ ምድር በምድረበዳው ከምስራቁ ባህር ጀምሮ እስከምዕራብ በሚከፍለው በቀጭኑ መንገድ፣ እናም በባህሩም ዳርቻና በምድረበዳው ዳርቻ፣ [ሀ]በዛራሔምላ በስተሰሜን በኩል በማንቲ ዳርቻ በሲዶም ወንዝ ምንጭ በኩል፣ ከምስራቅ ወደምዕራብ በሚፈሰው በኩል [ለ]አዋጅ ላከ—እናም ይህም ላማናውያንና ኔፋውያን የተከፈሉበት ነው።

፳፰ እንግዲህ፣ ብዙዎቹ የላማናውያን [ሀ]ስራ ፈቶች በምድረበዳው ውስጥ ኖሩ፣ እናም በድንኳን ኖሩ፤ በኔፊ ምድር ውስጥ በስተምዕራብ ምድረበዳው በኩልም ተዘረጉ፤ አዎን፣ እናም ደግሞ በዛራሔምላ ምድር በስተምዕራብ በኩል፣ በባህሩ ዳርቻና፣ በኔፊ ምድር በስተምዕራብ በመጀመሪያው የአባቶቻቸው የርስት ሥፍራ እናም በባህሩ ዳርቻ ነበሩ።

፳፱ እናም ደግሞ ኔፋውያን ካባረሩአቸው አካባቢ በባህሩ ዳርቻ በስተምስራቅ በኩል ብዙ ላማናውያን ነበሩ። እናም በዚያም ኔፋውያን ሙሉ በሙሉ በላማናውያን ሊከበቡ ተቃርበው ነበር፤ ይሁን እንጂ ኔፋውያን በምድረበዳው ወሰን በስተሰሜን በኩል፣ በሲዶም ወንዝ መነሻ፣ ከምስራቅ እስከምዕራብ፣ በምድረበዳው ዙሪያ ያሉትን ሥፍራዎች ተቆጣጥረዋል፣ በስተሰሜን በኩል፣ [ሀ]ለጋስ ብለው በሚጠሩት ምድር እስከሚመጡም ድረስ እንኳን ተቆጣጥረዋል።

፴ እናም ይህም ወደ ሰሜን የሚርቅ ሆኖ፣ የዛራሔምላ ህዝቦች በመጀመሪያ [ሀ]ያረፉበት ስፍራ በመሆኑ ያገኙበት [ለ]ስለአጥንታቸው የተናገርንባቸው ሰዎች ኖረውበት እናም ተደምሰሰውበት ወደነበረው ምድር ውስጥ እየገባ፣ [ሐ]የወደመ ስፍራ ብለው የሚጠሩትን ያዋስን ነበር።

፴፩ እናም እነርሱም በምድረበዳው በስተደቡብ በኩል መጡ። በስተሰሜን በኩል ያለው ቦታም [ሀ]የወደመው ስፍራ ተብሎ ይጠራ ነበር፣ እናም በስተደቡብ በኩል ያለው ምድር ለጋስ ተብሎ ይጠራል፣ ይህም በተለያዩ የዱር አውሬዎች ተሞልቶ የነበረ፣ ከፊሎቹም ምግብ ፍለጋ ከሰሜን በኩል የመጡ ነበሩበት፣ ምድረበዳው ነበር።

፴፪ እናም አሁን፣ ለኔፋውያን እስከ ለጋሱ ምድርና እስከ ወደመው ስፍራ ከባህሩ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ ርቀቱም የአንድ ቀን ተኩል [ሀ]ጉዞ ብቻ ነበር፤ እናም የኔፊና የዛራሔምላ ምድር ከሞላ ጎደል በውሃ የተከበበ ነበር፤ በስተሰሜንና በስተደቡብ ምድር መካከል [ለ]ቀጭን ሥፍራ ነበር።

፴፫ እናም እንዲህ ሆነ ኔፋውያን ለጋስን

፳፫ ሀ ቅ.መ.መ. መስበክ፣ ማስተማር፣ አስተማሪ፣ አገልግሎት።
ለ ቅ.መ.መ. መቀየር፣ የተቀየረ።
፳፯ ሀ ኦምኒ ፩፡ ፲፫–፲፯።
ለ አልማ ፳፫፡ ፩–፬።
፳፰ ሀ ፪ ኔፊ ፭፡ ፳፪–፳፭።
፳፱ ሀ አልማ ፶፪፡ ፱፣ ፳፫፡ ፭።
፴ ሀ ሔለ. ፯፡ ፲።
ለ ሞዛያ ፳፡ ፯–፲፪፣ ፳፰፡ ፲፩–፲፱።
ሐ አልማ ፶፡ ፴፬፣ ሞር. ፱፡ ፩–፫።
፴፩ ሀ ሔለ. ፫፡ ፭–፯።
፴፪ ሀ ሔለ. ፱፡ ፯።
ለ አልማ ፶፡ ፴፩።

ምድር፣ ከምስራቅ እስከ ምዕራቡ ባህር፣ ይኖሩበት ነበር፤ እናም ኔፋውያን ላማናውያን በስተሰሜን ምንም ሀብት እንዳይኖራቸው፣ በስተሰሜንም ያለውን ሥፍራ እንዳያጥለቀልቁት በብልሃታቸው ከጠባቂዎቻቸውና ከወታደሮቻቸው ጋር በስተደቡብ ባለው ሥፍራ አገዱአቸው።

፴፬ ስለዚህ በኔፊ ምድር እና በዙሪያው ካለው ምድረበዳ በስተቀር ላማናይቶች ምንም ይዞታዎች ሊኖራቸው አልቻሉም። ላማናውያን ለእነርሱ ጠላት በመሆናቸው፣ በየትኛውም አቅጣጫ አንዳያሰቃዩአቸው፣ እናም ደግሞ እንደፍላጎታቸው የሚሸሹበትን ሃገር ያገኙ ዘንድ እንግዲህ በኔፋውያን ይህ ብልህነት ነው።

፴፭ እናም አሁን እኔ፣ ይህን ካልኩኝ በኋላ፣ ወደ አሞንና አሮን፣ ኦምነርና ሂምኒ፣ እናም ወንድሞቻቸው ታሪክ በድጋሚ እመለሳለሁ።

ምዕራፍ ፴፫

የኃይማኖት ነፃነት ታወጀ—በሰባት ምድሮች እና ከተሞች ያሉ ላማናውያን ተሰወጡ—እራሳቸውንም አንቲ-ኔፊ-ሌሂዎች-ሌሂ ብለው ጠሩ፣ እናም ከእርግማኑ ነፃ ወጥተዋል—አማሌቂውያንና አሙሎናውያን እውነትን አልተቀበሉም። ከ፣ ፳–፳፪ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እነሆ እንግዲህ እንዲህ ሆነ የላማናውያን ንጉስ በአሞን፣ በአሮን፣ በኦምነር፣ በሂምኒ፣ እንዲሁም የእግዚአብሔርን ቃል በማንኛውም ቦታ በየትኛውም በምድሪቱ ክፍል ለመስበክ በሚሄዱት ወንድሞቻቸው ላይ እጃቸውን እንዳይጭኑ በህዝቦቹ ሁሉ መካከል [ሀ]አዋጅ ላከ።

፪ አዎን፣ ለማሰር እጃቸውን በእነርሱ ላይ በማድረግ ወይንም በወህኒ ቤት እንዳይጥሏቸው፣ ወይም እንዳይተፉባቸውም፣ እንዳይመቱአቸውም፣ ከምኩራባቸው እንዳያባርሩአቸውም፣ እንዳይገርፉአቸውም፣ ድንጋይም እንዳይወረውሩባቸውም፣ ነገር ግን ወደቤቶቻቸው እናም ደግሞ ወደ ቤተመቅደሶቻቸውና ወደተቀደሱት ስፍራዎቻቸው ውስጥ ለመግባት ነጻ ፍቃድ እንዲኖራው በመካከላቸው አዋጅ ላከ።

፫ እናም እንደዚህ እንደፍላጎታቸውም የጌታን ቃል እንደፍላጎታቸው ለመስበክ ይሄዱ ዘንድ፣ ምክንያቱም ንጉሱና ቤተሰቦቹ ወደጌታ ተለውጠዋልና፤ ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል የሚከላከለው እንዳይኖርበት ነገር ግን በምድሪቱ ላይ በሙሉ እንዲሆን፣ ህዝቡም መጥፎውን የአባቶቻቸውን [ሁ]ወግ ለማሳመን፣ እናም ሁሉም የእርስበርስ ወንድሞች መሆናቸውን እንዲያምኑ፣ ወይም እንዳይገድሉ፣ ወይም እንዳይዘርፉና፣ ወይም እንዳይሰርቁ፣ ወይም ዝሙትንም እንዳይፈፅሙ፣ ወይም ክፉ የሆኑትንም ነገሮች እንዳይፈፅሙ በምድሪቱ ላይ ሁሉ ለህዝቡ አዋጁን ላከ።

፬ እናም እንዲህ ሆነ ንጉሱ አዋጁን በላከ ጊዜ፣ አሮንና ወንድሞቹ ከከተማ ወደ ከተማ ተጓዙና፣ ከአንዱ ማምለኪያ ቦታ ወደ ሌላኛው በመጓዝ፣ ቤተክርስቲያኖችን በማቋቋም፣ እናም ካህናትንና መምህራን በላማናውያን ምድር በሙሉ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲሰብኩና እንዲያስተምሩ ቀደሱአቸው፤ እናም እንደዚህ ታላቅ ስኬትንም ማግኘት ጀመሩ።

፭ እናም በሺህ የሚቆጠሩ ጌታን ወደማወቅ መጡ፣ አዎን፣ በሺህ የሚቆጠሩት በኔፋውያን [ሂ]ባህል ወደማመንም መጡ፤ እናም እስከአሁኑ ጊዜ የተላለፉትን [ለ]መዝገቦችና ትንቢቶችም ተማሩ።

፮ እናም ጌታ ህያው እንደሆነ፣ በርግጥም ብዙዎች እንዳመኑትም፣ ወይም በራዕይና በትንቢት መንፈስ፣ እናም በውስጣቸው ድንቅ ስራን በሚሰራው በእግዚአብሔር ኃይል መሰረት በአሞንና በወንድሙ ሰበብ ብዙዎች እውነቱን ወደ ማወቅ የሚ

[ሀ] ሀ አልማ ፴፪፡፴፯። [ለ] ለ አልማ ፴፫፡፲፱። ቅ.መ.መ. ቅዱሳት መጻህፍት።
[ሁ] ሁ አልማ ፴፮፡፳፩። [ሂ] ሂ አልማ ፴፫፡፲፪።

መጡት—አዎን እንዲሁም እላችኋለሁ፣ ጌታ ህያው እንደሆነ፣ በስብከታቸው አም ነው የነበሩ ላማናውያን ሁሉ፣ እናም ወደ ጌታ ᵐተለውጠው የነበሩ፣ መንገዳቸውንም ᵃአልሳቱም ነበር።

፲፯ እነርሱም ፃድቃን ህዝቦች ሆኑ፣ ከእንግዲህ ከእግዚአብሔር ጋር እንዲሁም ከወን ድሞቻቸው ጋር እንዳይጣሉ የአመፅ መሣ ሪያቸውን ጣሉ።

፲፰ አሁን፣ ወደጌታም ᵐየተለወጡት እነ ዚህ ናቸው፡፡

፲፱ በእስማኤል ምድር የነበሩት የላማናው ያን ሕዝቦች፣

፲ እናም ደግሞ በሚዶኒ ምድር የነበሩት የላማናውያን ሕዝቦች፣

፲፩ እናም ደግሞ በኔፊ ከተማ የነበሩት የላ ማናውያን ሕዝቦች፤

፲፪ እናም ደግሞ በሼለም ምድር የነበሩ ትና፣ በሼምሎን ምድር የነበሩት፣ እናም በልሙኤል ከተማና፣ ᵐበሻምሎንም ከተማ የነበሩት የላማናውያን ሕዝቦች።

፲፫ እናም እነዚህ ወደጌታ ᵐየተለወጡት የላማናውያን ከተሞች ስም ነበሩ፤ እናም የአመፃቸውን መሳሪያዎች፣ አዎን፣ ሁሉ ንም የጦር መሳሪያዎቻቸውን የጣሉት እነዚህ ናቸው፤ እናም ሁሉም ላማናውያን ነበሩ።

፲፬ እናም ከአንዱ በስተቀር አማሌቂው ያን ᵐአልተለወጡም ነበር፤ ᵃከአሙሎና ውያንም ማንም አልተለወጠም፤ ነገር ግን ልባቸውን፣ ደግሞም በዚያ በከፊል በምድ ሪቱ፣ አዎን እናም መንደሮቻቸውን ሁሉና ከተሞቻቸውን ሁሉ የሚኖሩት ላማናውያን ልብም አጠጥረውት ነበር።

፲፭ ስለሆነም፣ ንስሃ የገቡባቸውንና እው ነትን እንዲያውቁ የተደረጉባቸውን እናም የተለወጡባቸውን የላማናውያን ከተሞች ሁሉ ሰይመናቸው።

፲፮ እናም አሁን እንዲህ ሆነ ንጉሱና የተ ለወጡት ከወንድሞቻቸው ተለይተው ይታ ወቁ ዘንድ ስም እንዲኖራቸው ፈለጉ፤ ስለ ዚህ ንጉሱ ከአሮንና ከብዙ ካህናቶቻቸው ጋር እነርሱ እንዲለዩ የሚሰጣቸውን ስም በተመለከተ ተመካከሩ።

፲፯ እናም እንዲህ ሆነ ስማቸውንም ᵐአንቲ-ኔፊ-ሌሂዎች በማለት ጠሩአቸው፤ እናም በዚህ ስም ተጠሩና፣ ከዚያን ጊዜ በኋላ ላማናውያን ተብለው አልተጠሩም።

፲፰ እናም ታታሪ ሰዎች መሆን ጀመሩ፤ አዎን፣ እናም ከኔፋውያን ጋር ወዳጅ ነበሩ፤ ስለዚህ ከእነርሱም ጋር ጓደኝነትን ጀመሩ፣ እናም የእግዚአብሔር ᵐእርግማን ከዚያን ጊዜ በኋላ አልተከተላቸውም።

ምዕራፍ ፳፫

ላማናውያን የእግዚአብሔር በሆኑት ሰዎች ላይ መጡ—አንቲ-ኔፊ-ሌሂዎች በክርስቶስ ተደሰቱ፣ እናም በመልአክት ተጎበኙ—እራሳቸውን ከመከላከል ይልቅ በሞት መሰቃየትን መረጡ—በርካታ ላማናውያን ተለወጡ። ከ፣ቀ–ፀ፣ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ አማሌቂውያንና፣ አሙሎናውያንም፣ በአሙሎን ምድር፣ ደግሞ በሔላም ምድር የነበሩት ላማናውያ ንም፣ እናም ᵐበኢየሩሳሌም ምድርና፣ በአ ጠቃላይ በምድሪቱ ሁሉ የነበሩት፣ ያልተ ለወጡት፣ እናም ᵃየአንቲ-ኔፊ- ሌሂን ስም ያልወሰዱት፣ በአማሌቂውያንና በአሙሎ ናውያን በወንድሞቻቸው ላይ ለማስቆጣት ተነሳስተው ነበር።

፪ እናም ጥላቻቸው በእነርሱ ላይ መሪር ነበር፤ እንዲህም ሆኖ በንጉሳቸውም ላይ እስከሚያምፁ ድረስ፣ እርሱ ንጉሳቸው እንዲሆን አልፈለጉም ነበር፤ ስለዚህ በአ ንቲ-ኔፊ-ሌሂዎች ህዝብ ላይም የጦር መሳ ሪያዎቻቸውን አነሱ።

፲፯ ᵐ ቅ.መ.መ. መቀየር፣ የተቀየረ።
ᵃ አልማ ፳፯፡፳፯።
፳ ᵐ አልማ ፳፯፡፲፣ ፴፩።
፲፪ ᵐ ሞዛያ ፳፪፡፳፡ ፲፩።
፲፫ ᵐ አልማ ፳፫፡፲።
፲፬ ᵐ አልማ ፳፬፡፳፱።
ᵃ አልማ ፳፫፡፴፩–፴፱።
፲፯ ᵐ ቅ.መ.መ. አንቲ-ኔፊ-ሌሂ።
፲፰ ᵐ ፩ ኔፊ ፪፡፳፫፣
፪ ᵐ ᵃ ኔፊ ፴፡፭–፮፣
፫ ᵐ ᵃ ኔፊ ፪፡፲፴–፲፯።
፳፬ ᵐ ᵃ አልማ ፳፬፡፩።
ᵃ አልማ ፳፭፡፩፣ ፲፫።

፲ እንግዲህ ንጉሱ በልጁ ላይ መንግስቱን አፀደቀ፣ እናም ስሙን አንቲ-ኔፊ- ሌሂ በማለት ጠራው።

፡ እናም ንጉሱ ላማናውያን በእግዚአብሔር ሰዎች ላይ ለጦርነት ዝግጅት በጀመሩበት ዓመት ሞተ።

፲፪ እንግዲህ አሞንና ወንድሞቹ እንዲሁም ከእርሱ ጋር የመጡት ሁሉ ላማናውያን ወንድሞቻቸውን ለማጥፋት መዘጋጀ ታቸውን በተመለከቱ ጊዜ፣ ወደ ምድያም ምድር መጡ፣ እናም እዚያ አሞን ወንድሞቹን በሙሉ ተገናኘ፤ እናም እራሳቸውን ከላማናውያን ለመከላከል ምን ማድረግ እንዳለባቸው ከላሞኒና ደግሞ ከአንቲ-ኔፊ-ሌሂዎች ጋር ᵐለመወያየት ወደ እስማኤል ምድር መጡ።

፲፫ እንግዲህ ወደ ጌታ ከተለወጡት ሰዎች መካከል በወንድሙ ላይ የጦር መሣሪያን የሚያነሳ አንድም ሰው አልነበረም፤ ለጦርነትም ቢሆን ምንም ዓይነት ዝግጅት ማንም አያደርግም፤ አዎን እናም ደግሞ ንጉሳቸው ለጦርነት እንዳይዘጋጁ አዟል።

፲፬ እንግዲህ፣ ይህንን በተመለከተ ለህዝቡ የተናገራቸው ቃላት እነዚህ ናቸው፥ የተወደዱትንም ሕዝቦቼን፣ ታላቁ አምላካችን በቸርነቱ እነዚህን ኔፋውያን ወንድሞቻችን ለእኛ እንዲሰብኩ፣ እናም የአባቶቻችንን ክፉ ᵐባህሎች እንዲያሳምኑን ስለላካቸው እግዚአብሔር አምላኬን አመሰግናለሁ።

፲፭ እናም እነሆ፣ ከእነዚህ ከኔፋውያን ወንድሞችም ጋር ጓደኝነት እንድንጀምር፣ ልባችንን ለማራራት የመንፈሱን ክፍል ስለላከልን ታላቁ አምላኬን አመሰግናለሁ።

፲፮ እናም እነሆ፣ ይህንን ጓደኝነት በመጀመር ᵐኃጢአታችንንና ብዙ ግድያዎችን መፈፀማችንን ስላመንን ደግሞ አምላኬን አመሰግናለሁ።

፲፯ እናም ለእነዚህን ነገሮች ንስሃ እንድንገባ ስለፈቀደልንና፣ ደግሞ ለፈፀምናቸው ኃጢአቶችና ግድያዎች ᵐይቅር ስላለን፣ እናም ᴬጥፋታችንን በልጁ አማካኝነት ከልባችን ስለወሰደው አምላኬን፣ አዎን ታላቅ የሆነውን አምላኬን አመሰግነዋለሁ።

፲፰ እናም አሁን እነሆ፣ ወንድሞቼ፣ (ከሰው ዘር ሁሉ በላይ የጠፋን እኛ በመሆናችን) ለኃጢአታችን ሁሉ እንዲሁም በር ካታ ግድያዎችን ለፈፀምንበት ንስሃ ለመግባት፣ እናም እነዚህን እግዚአብሔር ከልባችን ᵐእንዲያስወግድልን ለማድረግ የምንችለውን ሁሉ ይህ ብቻ ስለነበረ፣ ምክንያቱም በእግዚአብሔር ፊት በበቂ ሁኔታ ንስሃ ገብተን እርሱም ጥፋታችንን ሊወስድ በሚችልበት ሁሉ ልናደርግ የምንችለው ሁሉ ይህ ነበርና፤

፲፱ እንግዲህ፣ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ፣ እግዚአብሔር እንከናችንን በመውሰዱ፣ እናም ጎራዴዎቻችን ስላበሩ፣ ከእንግዲህ ጎራዴዎቻችንን በወንድሞቻችን ደም አናጎድፋቸው።

፲፲ እነሆ፣ እንዲህ እላችኋለሁ፣ አይሆንም፣ በወንድሞቻችን ደም እንዳይጎድፉ ዘንድ ጎራዴዎቻችንን እናስቀምጣቸው፤ ምናልባትም ጎራዴዎቻችንን በድጋሚ ካጎ ደፍናቸው ለኃጢአታችን ክፍያ በሚሆነው በታላቁ አምላካችን ልጅ ደም ከእንግዲህ ᵐሊነፁ አይችሉም ይሆናልና።

፲፰ እናም ታላቁ አምላክ በእኛ ላይ ምህረትንና፣ እንዳንጠፋ እነዚህን ነገሮች እና ድናውቃቸው አድርጓል፤ አዎን፣ እናም ᵐነፍሶቻችንን ልጆቻችንን ከመውደዱ ያህል ድረስ ስለሚወድ አስቀድሞ እነዚህን ነገሮች እንድናውቃቸው አድርጓል፤ ስለዚህ፣ ᴬየደህንነት ዕቅድ ለእኛ እንዲሁም ለወደፊቱ ትውልድ እንዲታወቅ በምህረቱ በመላዕክቱ ጎብኝቶናል።

፲፳ አቤቱ አምላካችን እንዴት መሀሪ

ᵉ ᴮ አልማ ፳፯፡ ፱–፲፫።
ᶠ ᴮ ሞዛያ ፩፡ ፫።
ᵍ ᴮ ት.እና ቃ. ፲፰፡ ፴፱።
ʰ ᴮ ዳን. ፱፡ ፱።
ᴬ ቅ.መ.መ. በደል።
ᴮ ᴮ ኢሳ. ፶፫፡ ፱–፯።
ᶜ ᴮ ራዕ. ፩፡ ፭።
ᵈ ᴮ ቅ.መ.መ. ነፍስ—የነፍሶች ዋጋ።
ᴱ ቅ.መ.መ. የቤዛነት ዕቅድ።

ነው! እናም አሁን እነሆ፣ ጉድፋችንን ከራ
ሳችን ለማስወገድ ይህን ያህል ብቻ ማድ
ረግ በመቻላችን እናም ጎራዴዎቻችን እን
ዲያበሩ በመደረጋቸው፣ ቃሉን ለእኛ ከሰ
ጠንና በዚህም ንጹህ ካደረገን በኋላ ጎራዴ
ያችንን በወንድሞቻችን ደም እንዳልበከልን
በመጨረሻው ቀን፣ ወይም በፊቱም እንዲ
ፈረድብን በምንቆምበት ቀን ለአምላካችን
ምስክር እንዲሆኑ፣ ጎራዴዎቻችን እያበሩ
እንድንጠብቃቸው እንደብቃቸው።

፲፯ እናም አሁን፣ ወንድሞቼ፣ ወንድሞ
ቻችን ሊያጠፉን ከፈለጉ፣ እነሆ፣ ጎራዴ
ዎቻችንን እንደብቃቸዋለን፤ አዎን፣ በመ
ጨረሻው ቀንም እንዳልተጠቀምንባቸው
ምስክር ይሆኑ ዘንድ አንፀባራቂ እንዲሆኑ
በመሬቱ ውስጥ እንደብቃቸዋለን፤ እናም
ወንድሞቻችን የሚያጠፉን ከሆነ፣ እነሆ፣
ወደ አምላካችን [ሀ]እንሄዳለንም፣ እንድና
ለንም።

፲፰ እናም አሁን እንዲህ ሆነ ንጉሱ ይህ
ንን አባባል በጨረሰና፣ ህዝቡም በአንድ
ላይ በተሰበሰበ ጊዜ፣ ጎራዴያቸውን፣ እናም
የሰው ደም ለማፍሰስ የሚያገለግሉትን መሳ
ሪያዎች ሁሉ ወሰዱና፣ በመሬት ውስጥም
[ለ]ቀበሩአቸው።

፲፱ እናም ይህንን ያደረጉት ከእንግዲህ
መሳሪያዎቹን የሰው ልጆችን ደም ለማፍ
ሰስ [ሐ]በድጋሚ እንደማይጠቀሙበት በእ
ነርሱ አመለካከት ለእግዚአብሔርና ለሰ
ዎች ምስክር እንዲሆን ነበር፤ እናም ይህን
ያደረጉት የወንድሞቻቸውን ደም ከማፍሰስ
ህይወታቸውን [መ]አሳልፈው እንደሚሰጡና፣
ከወንድም ከመውሰድ ይልቅ ለእርሱ መስ
ጠት እንደሚሻል ነበር፤ እናም ስራ በመ
ፍታት ጊዜያቸውን ከማሳለፍ በእጆቻቸው
ብዙ እንደሚሰሩ ለማረጋገጥና ከእግዚአብ
ሔርም ጋር [ሠ]ቃል ኪዳን ለመግባት ነው።

፲፱ እናም እነዚህ ላማናውያን እንዲያም
ኑና እውነትን እንዲያውቁ በመጡ ጊዜ፣
[ረ]የፀኑ እንደነበሩ፣ እናም ኃጢያትን ከመፈ
ፀም ሞት እንደሚሻላቸው እንደዚህ ተመ
ልክተናል፤ የሰላም መሳሪያዎቻቸውን እን
ደደበቁ፣ ወይም የጦርነት መሳሪያዎቻቸ
ውንም ለሰላም ሲሉ እንደደበቁ ተምልክ
ተናል።

፳ እናም እንዲህ ሆነ ወንድሞቻቸው
ላማናውያንም ለጦርነት ተዘጋጁና፣ ንጉሱን
ለማጥፋትና፣ ሌላውንም በቦታው ለመተ
ካት፣ እናም ደግሞ የአንቲ-ኔፊ-ሌሂዎች
ህዝቦችንም ከምድሪቱ ለማጥፋት ወደ ኔፊ
ምድር መጡ።

፳፩ እናም ህዝቡ ላማናውያን በእነርሱ ላይ
መምጣታቸውን በተመለከቱ ጊዜ ከእነርሱ
ጋር ለማገናኘት ሄዱና፣ በፊታቸውም ወደ
መሬት [ሠ]ዝቅ አሉላቸው፣ እናም የጌታን ስም
መጥራት ጀመሩና፤ ላማናውያን በእነርሱ
ላይ በመጡና በጎራዴው እነርሱን መግደል
በጀመሩ ጊዜ በዚህ ሁኔታ ነበሩ።

፳፪ እናም የሚቋቋማቸውን ሳያገኙ አንድ
ሺህ አምስት የሚሆኑትን ገደሉ፤ እናም እነ
ርሱ ከአምላካቸው ጋር ለመኖር በመሄዳ
ቸው የተባረኩ እንደሆኑ እናውቃለን።

፳፫ እናም ላማናውያን ወንድሞቻቸው
ከጎራዴው እንዳልሸሹ እንዲሁም ወደ
ቀኝም ሆነ ወደግራ ፈቀቅ አለማለታቸ
ውን፣ ነገር ግን እንደወደቁና እንደጠፉ፣
እናም በጎራዴው [ሰ]እየጠፉ እያለ አምላካ
ቸውን ማመስገናቸውን በተመለከቱ ጊዜ—

፳፬ እናም ላማናውያን ይህንን በተመለ
ከቱ ጊዜ እነርሱን ከመግደል [ሸ]ተገቱ፤ እናም
በጎራዴው ለወደቁት ወንድሞቻቸው በው
ስጣቸው ልባቸውም [ቀ]ያዘኑ ብዙዎች ነበሩ፣
ስላደረጓቸውም ነገሮች ንስሃ ገብተዋልና።

፳፭ እናም እንዲህ ሆነ የጦር መሳሪያዎ
ቻቸውን ጣሉና፣ በድጋሚ አይወሰዱአቸ
ውም፣ ምክንያቱም በፈፀሟቸው ግድያ
ዎች ተፀፅተዋልና፤ እናም እነርሱን ለመ
ግደል ክንዶቻቸውን በእነርሱ ላይ በሚያ

፲፯ ሀ አልማ ፴፡ ፲፩–፲፭።
፲፯ ለ ሔለ. ፲፭፡ ፱።
፲፰ ሀ አልማ ፶፫፡ ፲፩።
ለ ቅ.መ.መ. መስዋዕት።
ሐ ቅ.መ.መ. ቃል ኪዳን።
፲፱ ሀ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
፳፩ ሀ አልማ ፳፯፡ ፫።
፳፫ ሀ አልማ ፳፯፡ ፴፪።
፳፭ ሀ አልማ ፳፭፡ ፩።
ለ ቅ.መ.መ. ርህራሄ።

ነሱት ምህረት በመተማመን እንደ ወንድሞቻቸው ተንበረከኩ።

፳፮ እናም እንዲህ ሆነ ከተገደሉት በበለጠ የእግዚአብሔር የሆኑት በዚያን ቀን ተጨመሩ፤ እናም እነዚያ የተገደሉትም ፃድቃን ነበሩ፣ ነገር ግን እነርሱ [ሀ]እንደዳኑ ስለዚህ ለጥርጣሬ ምንም ምክንያት አልነበረንም።

፳፯ እናም ከእነርሱ መካከል ኃጢአተኛ የሆነ የተገደለ አልነበረም፤ ነገር ግን ከሺዎች የሚበልጡ እውነትን ወደማወቅ መጥተዋል፤ ስለዚህ ጌታ ለህዝቡ ደህንነት በብዙ [ሀ]መንገድ እንደሚሰራ እንመለከታለን።

፳፰ አሁን ብዙዎቹን ወንድሞቻቸውን የገደሉት ብዙ ቁጥር ያላቸው ላማናውያን አማሌቂውያን እና አሙሎናውያን ነበሩ፣ ብዙዎቹም [ሀ]የኔሆር [ለ]ስርዓትን የሚየሚከተሉ ነበሩ።

፳፱ እንግዲህ፣ የጌታን ሰዎች ከተቀላቀሉት መካከል፣ አማሌቂውያንም ሆነ አሙሎናውያን የተባሉ፣ በኔሆር ስርዓትም የሚጓዙ [ሀ]አልነበሩም፣ ነገር ግን እነርሱ የላማንና የልሙኤል ዝርያዎች ነበሩ።

፴ እናም ህዝቡ በጌታ መንፈስ አንዴ [ሀ]ከታነፁ፣ እናም ፅድቅን በሚመለከቱ ነገሮች ታላቅ [ለ]እውቀትን ካገኙ በኋላ፤ እናም ወደ ኃጢያትና መተላለፍ [ሐ]በመውደቃቸው ይበልጥ ጠጣሮች መሆናቸውንና፣ ሁኔታቸውም እነዚህን ነገሮች በጭራሽ የማያውቁ ከሚመስለው [መ]ይበልጥ የከፋ እንደሆነ በዚህ በግልጽ ለመለየት ይቻለናል።

ምዕራፍ ፳፭

የላማናውያን ወረራ ተስፋፋ—አቢናዲ እንደተነበየው የኖህ ካህናት ዝርያዎች ጠፉ—ብዙ ላማናውያን ተለወጡ፣ እናም ከአንቲ-ኔፊ-ሌሂዎች ሰዎችን ጋር ተቀላቀሉ—በክርስቶስ አመኑ እናም የሙሴን ህግ ጠበቁ። ከ፺–፸፯ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እነሆ፣ አሁን እንዲህ ሆነ ላማናውያን ወንድሞቻቸውን በመግደላቸው ይበልጥ ተናደዱ፤ ስለዚህ በኔፋውያን ላይ ለበቀል ማሉ፤ እናም በዚያን ጊዜ [ሀ]የአንቲ-ኔፊ-ሌሂዎች ሰዎችን ለመግደል ሙከራ አላደረጉም ነበር።

፪ ነገር ግን ወታደሮቻቸውን ወሰዱና፣ ወደ ዛራሔምላ ምድር ዳርቻ ሄዱ፣ እናም በአሞኒሀ ምድር ያሉትን ሰዎች አጠቁአቸው፣ እናም [ሀ]አጠፉቸው።

፫ እናም ከዚያን በኋላ ከኔፋውያን ጋር ብዙ ውጊያ ነበራቸው፣ በዚህም ተባረሩ በትና ተገደሉበት።

፬ እናም ከተገደሉት ላማናውያን መካከል [ሀ]የአሙሎንና የወንድሞቹ ዘሮች፣ የኖህ ካህናት የነበሩት ናቸው፣ እናም በኔፋውያን እጅ ነበር የተገደሉት፤

፭ እናም ቀሪዎቹ፣ በስተምስራቅ በኩል በምድረበዳው ከሸሹ በኋላ፣ እናም በላማናውያን ላይ ኃይላቸውንና ስልጣናቸውን ያለአግባብ በመያዛቸው፣ በርካታ ላማናውያን በእምነታቸው የተነሳ በእሳት [ሀ]እንዲጠፉ ተደረገ—

፮ [ሀ]ለብዙዎቹ፣ ብዙ ጥፋት ከደረሰባቸው እናም ከተሰቃዩ በኋላ፣ አሮንና ወንድሞቹ በምድራቸው የሰበኩትን [ለ]ቃል ማስታወስ ጀመሩ፤ ስለዚህ የአባቶቻቸውንም [ሐ]ወግ አለማመንና፣ በጌታ በማመን፣ እናም ለኔፋውያን ታላቅ ኃይልን እንደሰጣቸው ማመን ጀመሩ፤ እናም እንደዚህ ብዙዎች በምድረበዳው ውስጥ ተለውጠው ነበር።

፯ እናም እንዲህ ሆነ [ሀ]የአሙሎን ልጆች

፳፮ ሀ ራዕ. ፲፬፥፲፫።
፳፯ ሀ ኢሳ. ፶፭፥፰–፱፤
አልማ ፴፯፥፯–፯።
፳፰ ሀ አልማ ፩፥፲፭፤ ፪፥፩፣ ፰።
ለ አልማ ፳፩፥፬።
፳፱ ሀ አልማ ፳፫፥፲፬።
፴ ሀ ማቴ. ፲፪፥፵፭።
ለ ዕብ. ፲፥፳፮፤
አልማ ፵፯፥፴፮።
ሐ ፪ ኔፊ ፴፩፥፲፬፤
አልማ ፱፥፲፱።
ቅ.መ.መ. ክህደት።
መ ፪ ጴጥ. ፪፥፳–፳፩።
፳፭ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. አንቲ-ኔፊ-ሌሂ።
፪ ሀ አልማ ፰፥፲፮፤ ፲፮፥፱።
፬ ሀ ሞዛያ ፳፫፥፴፭።
፭ ሀ ሞዛያ ፲፯፥፲፭።
፮ ሀ ይህም ላማናውያን ማለት ነው።
ለ አልማ ፳፩፥፱።
ሐ አልማ ፳፮፥፳፬።
፯ ሀ አልማ ፳፩፥፫፤ ፳፬፥፩፣ ፳፰–፴።

ቅሪት የሆኑት ገዝዎች፣ እነርሱ፣ አዎን፣ በእነዚህ ነገሮች ሁሉ የሚያምኑት ᵃእንዲ ገደሉ አደረጉ።

፳ እንግዲህ ይህ ሰማዕት ብዙዎች ወን ድሞቻቸውን በቁጣ እንዲታወኩ አደረገ፤ እናም በምድረበዳው ፀብ ተጀመረ፤ ላማና ውያንም የአሙሎንን ዘር ᵇማደንና፣ መግ ደል ጀመሩ፤ እናም በምድረበዳው በስተ ምስራቅ በኩል ሸሹ።

፳፩ እናም እነሆ በዚህን ጊዜ እነርሱ በላ ማናውያን ታደኑ። ስለዚህ አቢናዲ በእሳት እንዲሞት ዘንድ ስላደረጉት የካህናቱ ዘሮች በተመለከተ የተናገረው ቃል ተፈፀመ።

፲ በእኔ ላይ ᵇየምታደርጉት ነገር ወደፊት ሊመጣ ያለው ነገር ምሳሌ ነው በማለት ተና ግሮአቸው ነበርና።

፲፩ እናም እንግዲህ ለእግዚአብሔር ባለው እምነት ለመጀመሪያ ጊዜ ሞትን ᵇበእሳት እንዲቀጣ የተደረገው አቢናዲ ነበር፤ አሁን እርሱ ይህን ማለቱ ነበር፣ እርሱ እንደተሰ ቃየው ብዙዎች በእሳት ሞት ይሰቃያሉ።

፲፪ እናም ለኖህ ካህናትም ዘሮቻቸው እር ሱን እንዳደረጉት ብዙዎችን በእሳት እን ደሚገድሉ፣ እናም ልክ እረኛ የሌላቸው በጎች እንደሚባረሩትና በዱር አውሬዎች እንደሚበሉት ወደሌላ ሀገርም እንደሚበ ታተኑና እንደሚገደሉ ነገራቸው፤ እናም አሁን እነሆ፣ ዘሮቻቸው በላማናውያን በመ ባረራቸው፣ በመታደናቸውና በመመታታ ቸው እነዚህ ቃላት ተረጋግጠው ነበር።

፲፫ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን ኔፋ ውያንን ማሸነፍ አለመቻላቸውን በተመ ለከቱ ጊዜ ወደራሳቸው ምድር ተመለሱ፤ እናም ብዙዎች በእስማኤል ምድርና በኔፊ ምድር ለመኖር ሄዱ፣ እናም ᵇአንቲ-ኔፊ-ሌሂዎች ከነበሩትም የእግዚአብሔር ሰዎች ጋር ተቀላቀሉ።

፲፬ እናም ወንድሞቻቸው እንዳደረጉት የጦር መሳሪያዎቻቸውን ᵇቀበሩና፣ ፃድቃን ህዝብም መሆን ጀመሩ፤ እናም በጌታ ጎዳና ተራመዱና፣ ትዕዛዛቱንና ህግጋቱን ጠበቁ።

፲፭ አዎን፣ እናም የሙሴን ህግ ጠብቀ ዋል፤ በአሁኑም ጊዜ ሁሉም ስላልተፈ ፀመ የሙሴን ህግ መጠበቅ አስፈላጊ ነበ ርና። ነገር ግን ᵇየሙሴ ህግ ቢኖርም የክ ርስቶስን መምጣት ይጠባበቁ ነበር፣ ምክ ንያቱም የሙሴ ህግ የመምጣቱ ᵃምልክት መሆኑን አስበው ስለነበር፣ እናም ክርስቶ ስም ለእነርሱ እስከሚገለጥ ድረስ ᵃየው ጪአዊውን ሥርዓታቸውን ማከናወን እን ዳለባቸው ስለሚያምኑ ነው።

፲፮ እንግዲህ ᵇደህንነትም በሙሴ ህግ እን ደሚመጣ አልገመቱም፤ ነገር ግን ᵃየሙሴ ህግ በክርስቶስ ያላቸውን እምነት ያጠ ነክራል፤ እናም እነዚያ ነገሮች ይመጣሉ ብሎ በተናገረው በትንቢት መንፈስ ᵃተስፋ በማድረግ፣ በእምነታቸው የዘለዓለማዊውን ደህንነት ተስፋ ያደርጋሉ።

፲፯ እናም አሁን እነሆ አሞንም፣ አሮ ንም፣ ኦምነርም፣ ሒምኒም፣ እናም ወን ድሞቻቸው በላማናውያን መካከል ድልን ስላገኙ፣ ጌታም ᵇእንደፀሎታቸው ስለሰ ጣቸውና ቃሉን ደግሞ በዝርዝር ስላረጋገ ጠላቸው እጅግ ተደሰቱ።

ምዕራፍ ፳፯

አሞን በጌታ ተመካ—ታማኞች በጌታ ይጠነክራሉ፣ እናም እውቀት ይሰጣቸ ዋል—ሰዎች በእምነት ሺህ ነፍሳትን ወደ ንስሃ ያመጣሉ—እግዚአብሔር ሁሉም ዓይነት ስልጣን አለው እናም ሁሉንም ያውቃል። ከ፣–ፍ፣ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም አሁን፣ አሞን ለወንድሞቹ የተ

፣ ᵃ ቅ.መ.መ. ሰማዕት፣ ሰማዕትነት።
፳ ᵇ ሞዛያ ፲፯፡ ፲፳።
፲ ᵇ ሞዛያ ፲፫፡ ፲።
፲፩ ᵇ ሞዛያ ፲፣፡ ፲፫።
፲፫ ᵇ አልማ ፳፫፡ ፲፣–፲፣።
፲፬ ᵇ አልማ ፳፬፡ ፲፭፣ ፳፣፡ ፴፪።
፲፭ ᵇ ያዕቆ. ፪፡ ፭፣ ጄረም ፩፡ ፲፩። ቅ.መ.መ. የሙሴ ህግ።
ᵃ ሞዛያ ፫፡ ፲፬–፲፭፣ ፲፣፡ ፲፬።
ᵃ ሞዛያ ፲፫፡ ፳፪–፴፪።
፲፣ ᵇ ሞዛያ ፲፪፡ ፴፩–፴፣፣ ፲፫፡ ፳፯–፴፫።
ᵃ ᵇ ሄለ ፪ ተሰ. ፭፡ ፳–፴።
ᵃ ᵇ ኔፊ ፲፩፡ ፬።
ᵃ ᵇ ፲፣ ᵇ አልማ ፲፣፡ ፴።

ናገራቸው ቃላት እነዚህ ናቸው፣ እንዲህም ይላሉ፥ ወንድሞቼ፣ እነሆ እንዲህ ብዬ እና ገራችኋለሁ፣ ለደስታችን እንዴት ታላቅ ምክንያት አለን፤ ከዛራሔምላ ምድር [ሀ]በጀ መርን ጊዜ እግዚአብሔር ታላቅ በረከትን ሊሰጠን እንደሚችል መገመት እንችላለን?

፪ እናም አሁን፣ እርሱ ምን ዓይነት ታላቅ በረከት በእኛ ላይ አድርጓል? ብዬ እጠይቃ ችኋለሁ፣ ይህንን ለመናገርስ ትችላላችሁን?

፫ እነሆ፣ እኔ እመልስላችኋለሁ፤ ወን ድሞቻችን፣ ላማናውያን በጨለማ ነበሩ፤ አዎን፣ እንዲያውም በጨለማው ገደል፤ ነገር ግን እነሆ፣ [ለ]ስንቶቹ ናቸው ድንቁን የእግዚአብሔር ብርሃን የተመለከቱት! እናም ይህንን ታላቅ ስራም ለመፈፀም በእ ግዚአብሔር እጅ [ሐ]መሳሪያ መሆናችን፣ ይህ በእኛ ላይ የወረደው በረከት ነው።

፬ እነሆ፣ [መ]ሺዎቹም ተደሰቱ፣ እናም ወደ እግዚአብሔር በረትም መጡ።

፭ እነሆ፣ [ሠ]እርሻው ተዘጋጅቶ ነበር፣ እናም እናንተ [ረ]ስላጨዳችሁና፣ በጉልበ ታችሁ ስለሰበሰባችሁ፣ አዎን፣ ቀኑን ሁሉ ስለሰራችሁ የተባረካችሁ ናችሁ፤ እናም [ሰ]የነዶዎቻችሁን ቁጥር ተመልከቱ! እናም እንዳይባክኑ በየጎተራዎቹ ይሰበሰባሉ።

፮ አዎን፣ እነርሱም በመጨረሻው ቀን በውሽንፍሩ አይመቱም፤ አዎን፣ [ሀ]በአ ውሎ ንፋሱም አይበታተኑም፤ ነገር ግን ውሽንፍሩ ሲመጣ ሁሉም በቦታቸው በአ ንድ ላይ ይሰበሰባሉ፣ ውሽንፍሩም ዘልቆ ሊገባ አይቻለውም፤ አዎን፣ በሃያሉ ነፋስ ጠላታቸው ሊወስዳቸው ወደሚፈልግበ ትም የትኛውም ቦታ ቢሆን አይገፉም።

፯ ነገር ግን እነሆ፣ እነርሱ [ለ]በአውድማው ጊታ እጅ ናቸው፣ እናም የእርሱ ናቸው፤ እርሱም በመጨረሻው ቀን [ሐ]ያስነሳቸዋል።

፰ የአምላካችን ስም የተባረከ ይሁን፤ [መ]በመዝሙር እናወድሰው፤ አዎን ለቅዱስ ስሙ [ሠ]ምስጋና እናቅርብ፤ ምክንያቱም እርሱ ለዘለዓለም ፅድቅን አድርጓልና።

፱ ከዛራሔምላ ምድር ባንመጣ ኖሮ፣ እነዚህ የተወደዱ ወንድሞቻችን፣ እኛንም እጅግ የሚወዱን፣ ለእኛ ያላቸው [ረ]ጥላቻ የከፋ ይሆን ነበር፣ አዎን እናም ደግሞ እነ ርሱ ለእግዚአብሔር ባዕዳን በሆኑ ነበር።

፲ እናም እንዲህ ሆነ አሞን እነዚህን ቃላት በተናገረ ጊዜ፣ ወንድሙ አሮን እንዲህ በማለት ወቀሰው፥ አሞን ደስታህ ወደኩ ራት ይወስድሃል ብዬ እፈራለሁ።

፲፩ ነገር ግን አሞን እርሱን እንዲህ አለው፥ በራሴ ጉልበት እንዲሁም በጥ በቤ [ሀ]አልኮራም፤ ነገር ግን እነሆ፣ [ለ]ደስ ታዬ ሙሉ ነው፣ አዎን፣ ልቤ በደስታ ይሞ ላል፣ እናም በአምላኬ ሐሴት አደርጋለሁ።

፲፪ አዎን፣ እኔ ምንም እንዳልሆንኩ አው ቃለሁ፤ ጉልበቴን በተመለከተ ደካማ ነኝ፤ ስለዚህ በራሴ [ሀ]አልኮራም፣ ነገር ግን በአ ምላኬ እኮራለሁ፣ ምክንያቱም በእርሱ [ለ]ኃይል ሁሉንም ነገር ማድረግ እችላለሁና፤ አዎን፣ እነሆ፣ በዚህ ምድር ብዙ አስደናቂ ተዓምራትን አድርገናል፣ ለዚህም ስሙን ለዘለዓለም እናወድሳለን።

፲፫ እነሆ፣ ስንት ሺህ ወንድሞቻችንን ነው እግዚአብሔር [ሀ]ከሲኦል እስራት የፈታው፣ እናም [ለ]የቤዛነትን ፍቅር እንዲዘምሩ ተደ ረጉ፣ እናም ለዚህም ምክንያቱ በውስጣችን ባለው በቃሉ ኃይል የተነሳ ነበር፣ ስለዚህ ለመደሰትስ ታላቅ ምክንያት አይኖረንምን?

፳፯ ፩ *ሀ* ሞዛያ ፳፰፡ ፱፤
አልማ ፲፯፡ ፯–፲፩።
፫ *ሀ* አልማ ፳፫፡ ፳–፲፫።
ለ ፪ ቆሮ. ፬፡ ፭፤
ሞዛያ ፳፫፡ ፲።
፬ *ሀ* አልማ ፳፫፡ ፭።
፭ *ሀ* ዮሐ. ፬፡ ፴፭–፴፯፤
ት.እና ቃ. ፬፡ ፬።
ለ ኢዩ. ፫፡ ፲፫።
ሐ ት.እና ቃ. ፴፫፡ ፯–፲፩፤
ሮ፭፡ ፪፤ ፭።
፯ *ሀ* ሔስ. ፭፡ ፲፪፤
፫ ኔፊ ፲፡ ፳፬–፳፯።
፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. መከር።
ለ ሞዛያ ፳፫፡ ፳፪፤
አልማ ፴፯፡ ፳፳።
፳ *ሀ* ት.እና ቃ. ፳፭፡ ፲፪።
ለ ቅ.መ.መ. አመስጋኝ፣
ምስጋናን፣ ምስጋና
መስጠት።
፴ *ሀ* ሞዛያ ፳፳፡ ፭–፪።
፲፩ *ሀ* ፪ ቆሮ. ፯፡ ፲፡
ለ ት.እና ቃ. ፲፳፡ ፲፡–፲፯።
ቅ.መ.መ. ደስታ።
፲፪ *ሀ* ኤር. ፱፡ ፳፬፤ አልማ ፳፱፡ ፱።
ለ መዝ. ፲፳፡ ፴፪–፴፣
ፊልጵ. ፬፡ ፲፫፤
፩ ኔፊ ፲፯፡ ፫።
፲፫ *ሀ* ቅ.መ.መ. ሲያል።
ለ አልማ ፭፡ ፳፯።

፲፬ አዎን፣ ልዑል እግዚአብሔር በመ ሆኑ እርሱን ለዘለዓለም ለማወደስ ምክን ያት አለን፣ እናም ወንድሞቻችንን ከሲኦል ᵐሰንሰለት አስለቅቋልና።

፲፭ አዎን፣ እነርሱም በዘለአለማዊው ጨለማና ጥፋት ተከበው ነበር፤ ነገር ግን እነሆ ወደ ዘለአለማዊው ᵐብርሃን፣ አዎን፣ ወደ ዘለአለማዊው ደህንነት አመጣቸው፤ እናም ወደር በሌለው ፍቅሩም ተከበዋል፤ አዎን እናም ይህን ታላቅና ድንቅ ስራ በመ ስራታችን በእጆቹ መሳሪያ ሆነን ነበር።

፲፮ ስለዚህ፣ እኛ ᵐእንደነቃለን፤ አዎን በጌታ ᵃእንደነቃለን፤ አዎን፣ ደስታችን ሙሉ በመሆኑ ሐሴት እናደርጋለን፤ አዎን አምላካችንን ለዘለዓለም እናወድሳለን። እነሆ፣ በጌታ ከመጠን በላይ ለመደነቅ የሚ ችል ማን ነው? አዎን፣ ስለታላቁ ኃይሉና፣ ᵃᵃስለምህረቱ፣ እናም ለሰው ልጆች ስላለው ፅናት አብዝቶ መናገር የሚችል ማን ነው? እነሆ እንዲህ እላችኋለሁ ከተሰማኝ ጥቂቱን ለመናገር አልችልም።

፲፯ አምላካችን ከአሰቃቂው ከኃጢያትና ከተበላሸው ሁኔታችን ሲያስለቅቀን እንደ ዚህ መሃሪ እንደሚሆንልን ማን ለመገመት ይቻለዋል?

፲፰ እነሆ፣ በቁጣም ቢሆን ቤተክርስቲ ያኗን በኃይል በማስፈራራት ᵐለማጥፋት ሄድን።

፲፱ አቤቱ እንግዲህ፣ ወደአሰቃቂው ጥፋት ለምን አልተወንም፣ አዎን፣ የፍ ርዱ ጎራዴስ በእኛ ላይ እንዲወድቅ፣ እናም ወደዘለዓለማዊው ጥፋት እንዲጥለን ለምን አላደረገም?

፳ አቤቱ ይህም ሀሣብ ነፍሴን እንድት ኮበልል አድርጓት ነበር፤ እነሆ፣ እግዚአ ብሔር ፍርዱን በእኛ ላይ አላደረገም፣ ነገር ግን በታላቁ ምህረቱ ᵐከዘለዓለማዊው ሞትና ስቃይ አሳልፎን፣ እንዲሁም ወደ ነፍሳችን ደህንነት አምጥቶናል።

፳፩ እናም አሁን እነሆ፣ ወንድሞቼ፣ እነ ዚህን ነገሮች የሚያውቅ ᵐተፈጥሯዊው ሰው ማን ነው? ንስሃ ከገባው በስተቀር እነዚህን ነገሮች ᵃየሚያውቅ ማንም የለም እላችኋ ለሁ።

፳፪ አዎን፣ ᵐንስሃ ለሚገቡ፣ ᵃእምነትን ለሚለማመደውና፣ መልካምን ለሚሰ ራው፣ እንዲሁም ሳያቋርጡ ለሚፀልየው፣ ለእንደእነዚህ ዓይነቶቹ ᵃᵃየእግዚአብሔርን ሚስጥር እንዲያውቁ ይሰጣቸዋል፤ አዎን፣ ለእንደነዚህ አይነቶቹ ተገልፀው የማያው ቁት ነገሮች እንዲገለፁላቸው ይሰጣቸዋል፤ አዎን እናም ለእነዚህ በሺህ የሚቆጠሩትን ነፍሳት ለንስሃ እንዲያመጡ ይሰጣቸዋል፣ እኛም ወንድሞቻችንን ለንስሃ እንድናመ ጣቸው እንደተሠጠን እንዲሁ ይሆናል።

፳፫ እናም ወንድሞቼ በዛራሔምላ ምድር ላሉት ወንድሞቻችን ወደኔፊ ምድር ለወን ድሞቻችን ለላማናውያን ለማስተማር እንሄ ዳለን እንዳልናቸው፣ እናም በማሾፍ እንደ ሳቁብን ታስታውሳላችሁን?

፳፬ እንዲህ ብለውናልና፥ ላማናውያ ንን እውነትን ወደማወቅ ማምጣት እንደ ሚቻላችሁ ትገምታላችሁን? እንደ ᵐአን ገተ ደንዳና ህዝቦች እንደነበሩት፤ በደም መፍሰስ ልባቸው እንደተደሰተው፤ ጊዜያ ቸውንም በክፋት እንዳሳለፉት፣ አቅጣጫ ቸውም ከመጀመሪያው ጀምሮ ሕጉን እን ደሚተላለፉት የሆነውን ላማናውያንን የአ ባቶቻቸው ᵃወግ ትክክል እንዳልነበር ለማ ሳመን ይቻለናል ብላችሁ ትገምታላችሁን? አሁን ወንድሞቼ ይህ የእነርሱ አነጋገር እን ደሆነ አስታውሱ።

፲፬ ᵐ አልማ ፲፪፡፲፭።
፲፭ ᵐ ቅ.መ.መ. ብርሀን፣ የክርስቶስ ብርሀን።
፲፮ ᵐ ሮሜ ፲፭፡፲፯፣
ᵃ ፪ ቆሮ. ፭፡፴፩።
ᵃᵃ ፪ ቆሮ. ፣ ፡ ፲፭–፲፰፣
ት.እና ቃ. ፫፯፡፰፩።
ᵃᵃᵃ መዝ. ፴፯፡፭–፮።
፲፰ ᵐ ሞዛያ ፳፯፡፳–፲።
፳ ᵐ ᵃ ኔፊ ፭፡፲፫፣
ሌለ. ፫፡፳፱–፴።
፳፩ ᵐ ቅ.መ.መ. ፍጥረታዊ ሰው።
ᵃ ፭ ቆሮ. ፪፡፱–፲፮፣
ያዕቆ. ፬፡ ፰።
፳፪ ᵐ አልማ ፴፮፡፬–፭።
ᵃ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣ ንስሀ
መግባት።
ᵃᵃ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
ᵃᵃᵃ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ሚስጥሮች።
፳፫ ᵐ ሞዛያ ፲፫፡፳፱።
ᵃ ሞዛያ ፣ ፡ ፲፭–፲፯።

፳፭ እናም በተጨማሪ እንዲህ አሉ፡ እነ ርሱንና ክፋታቸውን ከምድሪቱ እንድና ጠፋ፣ እኛንም እንዳይወሩን እናም እንዳ ያጠፉን መሳሪያዎቻችንን በእነርሱ ላይ እን ታጠቅ።

፳፮ ነገር ግን እነሆ፣ የተወደዳችሁ ወን ድሞቼ፣ ወደ ምድረበዳው የመጣነው ወን ድሞቻችንን ለማጥፋት ባለ ዓላማ አይደ ለም፣ ነገር ግን ጥቂት ነፍሳትን ለማዳን ባለ ዓላማ ነው።

፳፯ እናም ልባችን በተጨነቀ ጊዜና፣ ወደ ኋላችን ለመመለስ በተዘጋጀን ጊዜ፣ እነሆ፣ ጌታ [a]አፅናናን፣ እናም እንዲህ አለን፡ በወ ንድሞቻችሁ በላማናውያን መካከል ሂዱና፣ [b]ስቃያችሁን [c]በትዕግስት ያዙት፣ እናም መልካም ውጤትን እንድታገኙ አደርጋ ችኋለሁ።

፳፰ እናም አሁን እነሆ፣ እኛ መጥተና ልና፣ ከእነርሱ መካከል ሆነናል፤ እናም በስቃያችን ትዕግስተኞች ነበርንም፣ በማ ንኛውም የህይወት ውጣውረዶች ተሰቃ ይተናልም፤ አዎን፣ የዓለምን ምህረት ላይ ተስፋ በማድረግ ከቤት ወደቤት ተጉዘ ናል—በዓለም ምህረት ብቻ ሳይሆን በእ ግዚአብሔርም ምህረት ተስፋ አድርገናል።

፳፱ እናም በየቤቶቻቸው ገባንና፣ አስተ ማርናቸውም፣ በጎዳናዎቻቸው ላይ አስ ተማርናቸውም፤ አዎን፣ በኮረብታዎቻቸ ውም ላይ አስተማርናቸው፤ እናም፣ በቤ ተመቅደሶቻቸውና በምኩራባቸው ገባንም፣ አስተማርናቸውም፤ ተባረርንና፣ ተሳለቁ ብንም፣ ተፉብንም፣ ፈታችንንም መቱት፤ እናም በድንጋይ ተወገርንና ተወስደን በጠ ንካራ ገምዶች ታሰርን፣ ወደ ወህኒ ቤት ተጣልንም፤ እናም በእግዚአብሔር ኃይ ልና ጥበብ በድጋሚ ተለቀቅን።

፴ እናም በሁሉም ዓይነት ስቃይ ተሰቃ ይተናል፣ እናም ይህ ሁሉ የሆነውም ምና ልባት ጥቂት ነፍሳትን የምናድንበት መን ገድ እንድንሆን ነበር፤ እናም ምናልባት ጥቂቶችን ለማዳን ምክንያት ለመሆን ከቻ ልን [d]ደስታችን ሙሉ ይሆናል ብለን ገም ተን ነበር።

፴፩ እናም እነሆ፣ የስራችንን ፍሬ መመ ልከት እንችላለን፤ እናም እነርሱ ጥቂት ናቸውን? እኔ ግን አይደሉም እላችኋለሁ፤ እነርሱ [e]ብዙ ናቸው፤ አዎን ለወንድሞቻ ቸውና ደግሞ ለእኛ ባላቸው ፍቅር የተነሳ ከልባቸው መሆኑን እንመሰክራለን።

፴፪ እነሆም የጠላቶቻቸውን ነፍስ እንኳን ከማጥፋት ህይወታቸውን [f]መስዋዕት ማድ ረጉ ይሻላቸዋል፤ እናም ለወንድሞቻቸው ባላቸው ፍቅር የተነሳ የጦር መሳሪያዎቻ ቸውን በምድር ውስጥ በጥልቅ [g]ቀበሩት።

፴፫ እናም አሁን እንዲህ እላችኋለሁ፣ በምድሪቱ ሁሉ እንደዚህ ያለ ታላቅ ፍቅር አለን? እነሆ፣ እንዲህ እላችኋለሁ፣ በኔፋ ውያን መካከልም እንኳን የለም።

፴፬ እነሆም በወንድሞቻቸው ላይ መሣሪ ያዎቻቸውን ያነሳሉ፤ ነገር ግን እንዲገድሉ አቸው አይፈቅዱም። ነገር ግን እነሆ ከእ ነዚህ ስንቶቹ ናቸው ህይወታቸውን አሳል ፈው የሰጡት፤ እናም በፍቅራቸውና ለኃ ጢያት ባላቸው ጥላቻ ምክንያት ወደ አም ላካቸው መሄዳቸውን እናውቃለን።

፴፭ አሁን ለመደሰት ምክንያት የለን ምን? አዎን፣ እንዲህ እላችኋለሁ ከዓለም መፈጠር ጀምሮ እንደእኛ ለመደሰት ታላቅ ምክንያት ያላቸው ሰዎች በጭራሽ የሉም፤ አዎን፣ እናም ደስታዬ በአምላኬ እስከ ምኮራም እንኳን ደርሷል፤ ምክንያቱም እርሱ ሁሉም [h]ስልጣን፣ ሁሉም ጥበብ፣ እናም ሁሉም [i]ግንዛቤ አለውና፤ ሁሉንም ነገር ያውቃልና፣ እርሱ እስከ ደህንነትም እንኳን ንሰሃ ለሚገቡትና በስሙ ለሚያም ኑት [j]መሀሪ ነውና።

፴፮ እናም ይህ ኩራት ከሆነ፣ እኔም እን ደዛው እኮራለሁ፤ ምክንያቱም ይህ የእኔ

፳፯ *ሀ* አልማ ፲፯፡፱–፲፩።
ለ አልማ ፳፡፳፱–፴።
ቅ.መ.መ. ጭንቀት።
ሐ ቅ.መ.መ. ትዕግስት።

፴ *ሀ* ት.እና ቃ. ፲፰፡፲–፲፩።
፴፩ *ሀ* አልማ ፳፫፡፳–፲፫።
፴፪ *ሀ* አልማ ፳፩፡፳–፳፪።
ለ አልማ ፳፪፡፲፭።

፴፭ *ሀ* ቅ.መ.መ. ሀይል።
ለ ት.እና ቃ. ፹፰፡፴፭።
ሐ ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።

ህይወትና ብርሃን ነው፤ ደስታዬና ደህን ነቴ፣ እናም ከዘለዓለማዊው ጥፋት የእኔ ቤዛ ነውና። አዎን የእስራኤል ዛፍ ፡ቅር ንጫፍ ለሆኑት እናም በእንግዳው ምድር ለጠፉት ለዚህ ህዝብ የሚያስበው አምላክ ስሙ የተባረከ ይሁን፤ አዎን፣ እኛ በባዕድ ምድር ፡ለምንከራተተው የሚያስበው የአ ምላኬ ስም የተባረከ ይሁን እላለሁ።

፴፯ እንግዲህ ወንድሞቼ፣ እግዚአብ ሔር በየትኛውም ምድር ለሚገኙት ፡ህዝ ቦቹ እንደሚያስብ እንመለከታለን፤ አዎን፣ ህዝቡን ያስባል፣ እናም የአንጀት ምህረ ቱም በምድር ላይ ሁሉ ናቸው። እንግዲህ ይህ የእኔ ደስታና ታላቁ ምስጋናዬ ነው፤ አዎን፣ እናም ለአምላኬ ምስጋናዬን ለዘ ለአለም አቀርባለሁ። አሜን።

ምዕራፍ ፳፯

ጌታ አሞንን የአንቲ-ኔፊ-ሌሂዎች ሰዎች በደህንነት ወደሚቀመጡበት ቦታ እንዲ መራቸው አዘዘው—አልማን ባገኘው ጊዜ የአሞን ደስታ አቅም አሳጣው—ኔፋውያን ለአንቲ-ኔፊ-ሌሂዎች የኢየርሾንን ምድር ሰጡአቸው—እነርሱም የአሞን ህዝብ ተብለው ተጠሩ። ከ፣–፳፯ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እንግዲህ እንዲህ ሆነ ከኔፋውያን ጋር ለጦርነት የሄዱት እነዚያ ላማናውያን፣ እነ ርሱን ለማጥፋት ብዙ ከታገሉ በኋላ፣ ጥፋ ታቸውን መሻት ከንቱ ሆኖ ባገኙት ጊዜ፣ በድጋሚም ወደኔፊ ምድር ተመለሱ።

፪ እናም እንዲህ ሆነ አማሌቂውያን፣ በደረሰባቸው ሽንፈት ምክንያት እጅግ ተቆጡ። እናም ኔፋውያንን ለመበቀል እን ዳልቻሉ በተመለከቱ ጊዜ፣ ፡በወንድሞቻ ቸው ፡በአንቲ- ኔፊ-ሌሂ ህዝቦች ላይ ሰዎ ችን በቁጣ ማነሳሳት ጀመሩ፤ ስለዚህ በድ ጋሚ እነርሱን ማጥፋት ጀመሩ።

፫ እንግዲህ እነኚህ ህዝቦች ፡በድጋሚ መሳሪያዎቻቸውን ለማንሳት እምቢተኞች ሆኑ፣ እናም በጠላቶቻቸው ፍላጎት መሠ ረት ለመሞት ፈቃደኞች ሆኑ።

፬ እንግዲህ አሞንና ወንድሞቹ በተወደዱ ባቸው እናም እጅግ በወደዱአቸው መካከል ይህን የጥፋት ስራ በተመለከቱ ጊዜ—ከዘ ለዓለማዊው ጥፋት እነርሱን ለማዳን እን ደመልአክ ከእግዚአብሔር እንደተላኩ ተመስለዋልና—ስለዚህ፣ አሞንና ወንድ ሞቹ ይህን ታላቅ ጥፋት በተመለከቱ ጊዜ፣ እጅግ አዘኑ፣ እናም ፡ለንጉሱ እንዲህ ሲሉ ተናገሩ፥

፭ እነኚህን የጌታ የሆኑትን ሰዎች በአንድ ላይ እንሰብስባቸው፣ እናም ወደ ኔፋውያን ወንድሞቻችን ወደ ዛራሔምላ ምድር እን ውረድና፣ እንዳንጠፋ ከጠላቶቻችን እጅ እናምልጥ።

፮ ነገር ግን ንጉሱ እንዲህ አላቸው፥ እነሆ፣ ብዙ ግድያዎችንና ኃጢያቶችን በእ ነርሱ ላይ በመፈፀማችን ኔፋውያን ያጠፉ ናል።

፯ እናም አሞን እንዲህ አለ፥ እሄዳለሁና፣ ጌታን እጠይቀዋለሁ፣ እናም እርሱ ወደ ወንድሞቻችን ሂዱ ቢለን፣ ትሄዳላችሁን?

፰ እናም ንጉሱ እንዲህ አለው፥ አዎን፣ ጌታ ሂዱ ብሎ ከተናገረን፣ ወደ ወንድሞ ቻችን እንሄዳለን፣ እናም በእነርሱ ላይ የፈ ፀምናቸውን ግድያዎችና ኃጢአቶች እስከ ንክስ አገልጋዮቻቸው እንሆናለን።

፱ ነገር ግን አሞን እንዲህ አለው፥ በወን ድሞቹ መካከል ማንንም ፡በባርነት መያዝ በአባቴ ከተመሰረተው ህግ ላይ ተቃራኒ ነው፤ ስለዚህ እንሂድ እናም በወንድሞቻ ችን ምህረት ላይ እንመካ።

፲ ነገር ግን ንጉሱ እንዲህ አለው፥ ጌታን ጠይቅ፣ እናም እርሱ ሂዱ ካለን እንሄዳለን፤ አለበለዚያ በምድሪቱ እንጠፋለን።

፴፯ ሀ ዘፍጥ. ፵፱፡ ፳፪–፳፯፤ ያዕቆ. ፪፡ ፳፭፤ ፭፡ ፳፭።
ለ ያዕቆ. ፯፡ ፳፯።
፴፯ ሀ የሐዋ. ፲፡ ፴፱–፴፭፤ ፪ ኔፊ ፳፯፡ ፴፫።
፳፯ ፪ ሀ አልማ ፴፫፡ ፲፩።
ለ አልማ ፳፭፡ ፩።
ቅ.መ.መ. አንቲ-ኔፊ-ሌሂ። ፫ ሀ አልማ ፳፱፡ ፳፩–፳፯።
፬ ሀ አልማ ፳፱፡ ፭።
፱ ሀ ሞዛያ ፪፡ ፲፫፣ ፳፱፡ ፴፪፣ ፴፰፡ ፵።

፲፩ እናም እንዲህ ሆነ አሞን ሄደና ጌታን ጠየቀ፣ ጌታም እንዲህ አለው፥

፲፪ ይህ ህዝብ እንዳይጠፉ ከዚህ ምድር አስወጣቸው፣ ምክንያቱም ላማናውያን ወንድሞቻቸውን ለመግደል በሚያውኩ አማሌቂውያን ልብ ሰይጣን በሀይል ይዞ ታልና፤ ስለዚህ ከዚህ ምድር ውጣ፤ እናም በዚህ ትውልድ ያለ ህዝብ የተባረከ ነው፣ እጠብቀዋለሁና።

፲፫ እናም አሁን እንዲህ ሆነ አሞን ጌታ የተናገረውን ቃል ሁሉ ሄዶ ለንጉሱ ተናገረ።

፲፬ እናም ህዝቦቻቸውን በአንድ ላይ ሰበሰቡ፤ አዎን፣ የጌታ የሆኑትን ሰዎች በሙሉ፣ እናም ከብቶቻቸውንና መንጋዎቻቸውን በሙሉ በአንድ ላይ ሰበሰቡ፣ እናም ከምድሪቱ ወጥተው ሄዱና፣ የኔፊን ምድር ከዛራሔምላ ምድር ወደሚከፍለው ምድረበዳ ደረሱ፣ ወደ ምድሪቱ ዳርቻ አጠገብም ደረሱ።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ አሞን እንዲህ አላቸው፥ እነሆ፣ እኔና ወንድሞቼ ወደ ዛራሔምላ ምድር እንሄዳለን፣ እናንተም እኛ እስከምንመለስ ድረስ እዚህ ትቆያላችሁ፤ እናም በምድራቸው እንድትመጡ እንዲፈቅዱ የልብ ፍላጎታቸውን ለማወቅ እንሞክራለን።

፲፮ እናም እንዲህ ሆነ አሞን ወደ ምድሪቱ በሄደ ጊዜ፣ እርሱና ወንድሞቹ [ሀ]በተነገረው ቦታ አልማን አገኙት፤ እናም እነሆ፣ ይህም አስደሳች ግንኙነት ነበር።

፲፯ እንግዲህ የአሞን [ሀ]ደስታ ሙሉ እስኪሆን ታላቅ ነበር፤ አዎን፣ በአምላኩም ደስታ ተውጦ ነበር፤ [ለ]ጉልበቱ እንኳን እስከሚደክም ድረስ፤ እናም [ሐ]በድጋሚ በመሬት ላይ ወደቀ።

፲፰ እንግዲህ ይህ ታላቅ ደስታ አይደለምን? እነሆ እውነተኛ ንስሀ ገቢ እና ትሁት ደስታን ፈላጊ ካልሆነ በቀር ማንም የማይቀበለው ደስታ ነው።

፲፱ እንግዲህ አልማ ወንድሞቹን በማግኘቱ ደስታው በእውነት ታላቅ ነበር፤ እናም ደግሞ የአሮን፣ ኦምነርና፣ የሄምኒ ደስታ ታላቅ ነበር፤ ነገር ግን እነሆ ደስታቸው ከጉልበታቸው በላይ አልነበረም።

፳ እናም እንዲህ ሆነ አልማ ወንድሞቹን ወደ ዛራሔምላ ምድር፣ እንዲሁም ወደ ራሱ ቤትም፣ በመምራት መለሳቸው። እናም ሄዱና፣ በወንድሞቻቸው በላማና ውያን መካከል በኔፊ ምድር የሆኑትን ነገሮች [ሀ]ለዋናው ዳኛ ተናገሩ።

፳፩ እናም እንዲህ ሆነ ዋናው ዳኛ የአንቲ-ኔፊ-ሌሂዎች ሰዎች የሆኑትን በምድሪቱ ይገቡ ዘንድ በሚመለከት የህዝብን ድምፅ ለመፈለግ በምድሪቱ ሁሉ አዋጅ ላከ።

፳፪ እናም እንዲህ ሆነ የህዝቡ ድምፅ እንዲህ በማለት መጣ፥ እነሆ፣ በባህሩ በስተምስራቅ በኩል ያለው ለጋስን ምድር የሚያገናኘውን፣ በለጋስም ምድር በስተደቡብ ያለው የኢየርሾንን ምድር እንተዋለን፤ እናም ይህ የኢየርሾን ምድር እንዲወርሱት ለወንድሞቻችን የምንሰጠው ምድር ነው።

፳፫ እናም እነሆ፣ በኢየርሾን ምድር ወንድሞቻችንን እንጠብቃቸው ዘንድ በኢየርሾንና በኔፊ ምድር መካከል ወታደሮቻችንን እናስቀምጣለን፤ እናም ይህን ለወንድሞቻችን የምናደርገው በወንድሞቻቸውም ላይ መሳሪያዎቻቸውን በማንሳት ኃጢያት እንዳይፈፅሙ ባላቸው ፍርሀት ምክንያት ነው፤ እናም ይህ ታላቅ ፍርሃት የመጣው ለበርካታ ግድያዎቻቸውና አሰቃቂ ኃጢአታቸው ከገቡት መሪር ንስሃ የተነሳ ነው።

፳፬ እናም አሁን እነሆ፣ የኢየርሾንን ምድር ይወርሱ ዘንድ ይህንን ለወንድሞቻችን እናደርጋለን፤ እናም ወታደሮቻችንን ለማቆየት የምንረዳበት ነገር የሚሰጡን ከሆነ በወታደሮቻችን ከጠላቶቻቸው እንጠብቃቸዋለን።

፲፯ ሀ አልማ ፲፯፡ ፩–፬።
፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. ደስታ።
ለ ፩ ኔፊ ፩፡ ፯።
ሐ አልማ ፲፱፡ ፲፬።
፳ ሀ አልማ ፬፡ ፲፯–፲፰።

፳፭ እናም እንዲህ ሆነ አሞን ይህንን በሰማ ጊዜ፣ ወደ አንቲ-ኔፊ-ሌሂዎች ሰዎች ተመ ለሰ፣ ደግሞም አልማ ከእርሱ ጋር ድንኳ ናቸውን በተከሉበት ምድረበዳ ተመለ ሱና፣ ይህንን ነገር ሁሉ እንዲያውቁ አደ ረጉአቸው። እናም አልማ ከአሞንና፣ ከአ ሮን እንዲሁም ከወንድሞቹ ጋር የእርሱን [ሀ]መለወጥ ተረከላቸው።

፳፮ እናም እንዲህ ሆነ ይህ ነገርም በመ ካከላቸው የታላቅ ደስታ መንስኤ ነበር። እናም ወደ ኢየርሾን ምድር ሄዱና፣ የኢ የርሾን ምድርን በባለቤትነት ወሰዱ፤ እናም በኔፋውያን የአሞን ህዝብ ተብለው ተጠሩ፤ ስለዚህ ከዚያን ጊዜም በኋላ በዚህ ስም ተለ ይተው ይታወቃሉ።

፳፯ እናም እነርሱ ከኔፊ ህዝብ ጋር ነበሩ፣ ደግሞም የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ከነበሩት ሰዎች ጋር ተቆጠሩ። እናም ለእ ግዚአብሔርና፣ ደግሞ ለሰዎች ባላቸው ቅንአት ይለዩ ነበር፤ ምክንያቱም በሁሉም ነገር ፍፁም [ሀ]ታማኝና ቀጥተኞች ነበሩ፤ እናም እስከመጨረሻ በክርስቶስ እምነት [ለ]ፅኑ ነበሩ።

፳፰ እናም የወንድሞቻቸውን ደም ማፍ ሰስን በታላቅ ጥላቻ ተመለከቱ፤ በወንድ ሞቻቸው ላይ መሣሪያን ለማንሳትም በጭ ራሽ ሊገፋፉ አይቻሉም፤ እናም በክርስቶ ስና በትንሳኤው ባላቸው ተስፋና ግንዛቤ፣ ሞትን በፍርሃት ደረጃ በጭራሽ አልተመለ ከቱም፤ ስለዚህ ሞታቸው በክርስቶስ ሞት ድል ተነስቷል።

፳፱ ስለዚህ ወንድሞቻቸውን ለመምታት ጎራዴውን እንዲሁም ሻቡላውን ከመውሰ ዳቸው በፊት በወንድሞቻቸው ሊደርስባ ቸው በሚችል እጅግ በሚያሰቅቅና በሚያ ሰቃይ ሁኔታ [ሀ]ሞትን ይቀበላሉ።

፴ እናም እነርሱ ቅንዓት ያላቸውና የተ ወደዱ ሰዎች፣ በጌታም እጅግ የተወደዱ ሰዎች ነበሩ።

ምዕራፍ ፳፰

ላማናውያን በአስገራሚው ውጊያ ተሸ ነፉ—በሺዎች የሚቆጠሩ ሞቱ—ኃጢአ ተኞች ማብቂያ ለሌለው መከራ ይሰጣሉ፤ ፃድቃኖች ማብቂያ የሌለውን ደስታ ያገ ኛሉ። ከ፳፩–፳፭ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም አሁን እንዲህ ሆነ የአሞን ህዝብ [ሀ]በኢየርሾን ምድር ከሰፈሩ፣ እናም ደግሞ ቤተክርስቲያንም ካቋቋሙባት በኋላ፣ የኔ ፋውያን ወታደሮች በኢየርሾን ምድር ዙሪያ፣ አዎን፣ በዛራሔምላ ምድር ዳርቻ ዙሪያ ተመደቡ፤ እነሆ የላማናውያን ወታ ደሮች ወንድሞቻቸውን በምድረበዳው ተከትለዋቸው ነበር።

፪ እናም በዚያ አስገራሚ ውጊያ ነበር፤ አዎን፣ በሁሉም ህዝብ መካከል ሌሂ ኢየ ሩሳሌምን ለቆ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ታይቶ የማይታወቅ አይነት እንኳን፤ አዎን፣ እናም በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ላማናውያን ተገ ደሉ፣ ወደ ውጪም ተበተኑ።

፫ አዎን፣ እናም ደግሞ በኔፋውያን መካ ከል አስገራሚ ግድያ ነበር፤ ይሁን እንጂ፣ ላማናውያን [ሀ]ተባረሩና ተበታተኑ፣ እናም የኔፊ ህዝብ በድጋሚ ወደ ሥፍራቸው ተመ ለሱ።

፬ እናም አሁን ይህ ታላቅ ሀዘንና ልቅሶ በኔፋውያን ህዝብ ሁሉ መካከል የተሰማ በት ጊዜ ነበር—

፭ አዎን፣ ባልቴቶቹ ለባሎቻቸው፣ ደግ ሞም አባቶች ለወንድ ልጆቻቸውና፣ ሴት ልጅ ለወንድሟ፣ አዎን፣ ወንድምም ለአ ባቱ በማዘን ልቅሶአቸው ተሰምቷል፤ እናም የሀዘን ለቅሶ በሁሉም መካከል ተሰ ምቷል፣ ለተገደሉ ወገኖቻቸው ሁሉ ሀዘን ነበር።

፮ እናም አሁን ይህ አሳዛኝ ቀን ነበር፤ አዎን፣ የማስተዋልም ጊዜና፣ እጅግ [ሀ]የሚ ጾምበትና የሚጸለይበት ጊዜ ነበር።

፳፭ ሀ ሞዛያ ፳፯፡፲–፳፬።
፳፯ ሀ ቅ.መ.መ. ታማኝ፣ ታማኝነት።
ለ አልማ ፳፫፡፮።
፳፱ ሀ አልማ ፳፬፡፳–፳፫።
፳፰ ፩ ሀ አልማ ፳፯፡፳፪፣
፩ ሀ አልማ ፴፡፩፣ ፲፱።
፫ ሀ አልማ ፴፡፩።
፮ ሀ አልማ ፴፡፪።

፲ እናም በዚህ በኔፊ ህዝብ መካከል አሥራ አምስተኛው የመሳፍንት አገዛዝ አበቃ፤

፲፩ እናም ይህ አሞንና ወንድሞቹ በኔፊ ምድር ውስጥ የነበራቸው ጉዞአቸው፣ በምድሪቱ ስቃያቸው፣ ሀዘናቸውና መከራቸው፣ እናም [ሀ]ለማስተዋል የማይቻል ደስታቸው፣ እንዲሁም በኢየርሾን ምድር ያሉ ወንድሞች አቀባበላቸውና ደህንነታቸው ታሪክ ነው። እናም አሁን የሰው ልጆች ሁሉ አዳኝ ጌታ ለዘለዓለም ነፍሳቸውን ይባርክ።

፲፪ እናም ይህ በኔፋውያን መካከል የነበረው ፀብና ደግሞ በኔፋውያንና በላማናውያን መካከል የነበረው ጦርነት ታሪክ ነው፤ እናም አሥራ አምስተኛው የመሳፍንት አገዛዝ በዚሁ ተፈፀመ።

፲፫ እናም ከመጀመሪያው ዓመት ጀምሮ እስከ አሥራ አምስተኛው ዓመት ድረስ በሺህ የሚቆጠሩ ነፍሳት ጠፍተዋል፤ አዎን፣ አሰቃቂ የደም መፍሰስም ነበር።

፲፬ እናም በሺህ የሚቆጠሩት ሰውነቶች በምድር ውስጥ ሲቀበሩ ብዙዎች ደግሞ በሺህ የሚቆጠሩት በምድር ገፅ ተቆልለው [ሀ]በስብሰዋል፤ አዎን፣ እናም ብዙ ሺህዎች ለአለቁት ወገኖቻቸው [ለ]አዝነዋል፣ ምክን ያቱም በጌታ ቃል ኪዳን መሰረት በዚያም መጨረሻ ለሌለው ስቃይ እንደተመደቡ የመፍራት ምክንያት ነበራቸውና።

፲፭ ሌሎች ብዙ ሺዎች ዘሮቻቸው በመጥፋታቸው ቢያዝኑም፣ ነገር ግን በተስፋ፣ እናም በጌታ [ሀ]ቃል ኪዳን መሰረት መጨረሻ በሌለው ደስታ በእግዚአብሔር ቀኝ እጅ በኩል ለመኖር እንደሚነሱ በማወቃቸው ይደሰቱ፣ እናም ሐሴት ያደርጉ ነበር።

፲፮ እናም በኃጢያትና በመተላለፍምና የሰው ልጆችን የልብ ለማጥመድ ብልህ በሆነው [ሀ]እቅዱ በሚመጣው በዲያብሎስ ሀይል ምክንያት የሰዎችን [ለ]ልዩነት ታላቅ ነቱን እንዴት እንደሆነ እንደዚህ ለመመል ከት ይቻለናል።

፲፯ እናም በጌታ [ሀ]የወይን ስፍራ ሰዎች እን ዲሰሩ ታላቁን የትጋት ጥሪ እንደዚህ እንመ ለከታለን፤ እናም የታላቁን ሀዘንና፣ ደግሞ የደስታን መንስኤ ምክንያትንም እንደዚህ እንመለከታለን—በሞቱና በሰዎች መጥ ፋት የተነሳ ሃዘን፣ እናም በክርስቶስ የህ ይወት [ለ]ብርሃንም ምክንያት ደስታን እን መለከታለን።

ምዕራፍ ፳፱

አልማ በመለኮታዊ ቅንዓት ንስሃን ለመ ጮህ ፈለገ—ጌታ ለሁሉም ሀገር አስተማ ሪዎችን ሰጠ—አልማ በጌታ ስራ፣ እናም በአሞንና በወንድሞቹ ስኬታማነት ተደ ሰተ። በ፳፯ ም.ዓ. ገደማ።

፩ አቤቱ፣ እንድሄድ እናም ምድሪቱን በሚያንቀጠቅጠው ድምፅ፣ በእግዚአብ ሔር መለከት እናገር ዘንድና ለማንኛውም ሰው ንስሃን እናገር ዘንድ፣ መልዓክ በሆን ኩና የልቤም መሻት በሞላልኝ!

፪ አዎን፣ ንስሃ እንዲገቡና [ሀ]ወደአምላ ካችን እንዲመጡ፣ በምድሪቱ ገፅ ላይም ከዚህ የበለጠ ሀዘን እንዳይኖር፣ እንደነጎ ድጓድም ድምፅ ለማንኛውም ነፍስ ንስሃን እናም የቤዛነትን ዕቅድ አውጅ ነበር።

፫ ነገር ግን እነሆ፣ እኔ ሰው ነኝ፤ እናም በፍላጎቴ ኃጢያትን እሰራለሁ፤ ምክንያ ቱም ጌታ በሰጠኝ ነገሮች መረካት ይገባ ኛልና።

፬ ጠንካራ የሆነውን ፍትሀዊውን የአም ላክ አዋጅ በፍላጎቴ መለወጥ አይገባኝም፣ ምክንያቱም ለህይወታቸውም ይሁን ለሞ ታቸው [ሀ]እንደፍላጎታቸው እርሱ እንዲሰ ጣቸው አውቃለሁ፤ አዎን ለሰዎች እንደ [ለ]ፈቃዳቸው ለደህንነትም ይሁን ለጥፋት

፳ ሀ አልማ ፳፯፡ ፲፯–፲፱።
፲፩ ሀ አልማ ፲፯፡ ፲፩።
ለ አልማ ፴፳፡ ፳፫፤ ት.እና ቃ. ፴፪፡ ፴፩–፴፯።
፲፪ ሀ አልማ ፲፩፡ ፴፩።
፲፫ ሀ ፪ ኔፊ ፱፡ ፳፳።
ለ ፩ ኔፊ ፲፯፡ ፴፭።
፲፬ ሀ ቅ.መ.መ. የጌታ የወይን አትክልት ስፍራ።
ለ ቅ.መ.መ. ብርሀን፣ የክርስቶስ ብርሀን።
፳፱ ፪ ሀ ኦሞኒ ፩፡ ፳፯፤ ፫ ኔፊ ፳፩፡ ፳።
፬ ሀ መዝ. ፴፯፡ ፬።
ለ ቅ.መ.መ. ነጻ ምርጫ።

መደብ፣ አዎን መለወጥ የማይችል አዋጅ በማወጅ እንደሚሰጣቸው አውቃለሁ።

፮ አዎን፣ እናም መልካምና መጥፎ የሆ ነው በሰዎች ሁሉ ፊት እንደመጣ አውቃ ለሁ፤ መልካሙን ከመጥፎው የማያውቅ እንከን የለሽ ነው፤ ነገር ግን መልካምና መጥፎውን ᵐለሚያውቅ ለእርሱ እንደፍላ ጎቱ፣ ፍላጎቱ መልካምም ይሁን መጥፎ፣ ህይወትም ይሁን ሞት፣ ደስታም ይሁን ᵃየህሊና ፀፀት ይሰጠዋል።

፯ እንግዲህ፣ እነዚህን ነገሮች ማወቁን በመመልከት፤ ከተጠራሁበት የበለጠ ስራስ ለማከናወን ለምን እፈልጋለሁ?

፰ ለምንስ መልአክ ሆኜ እስከምድር ዳርቻ መናገር እስከምችል እመኛለሁ?

፱ እነሆም ጌታ ᵐለሀገሮች ሁሉ ቃሉን በጥ በብ፣ አዎን፣ ሊኖራቸው ᵃየሚገባውን ነገር ሁሉ እንዲያስተምሩ የራሳቸውን ሀገር እና ᵇቋንቋ ሰጥቷል፤ ስለዚህ ጻድቅና እውነት በሆነው መሰረት ጌታ በጥበቡ እንደሚመ ሰክር እንመለከታለን።

፲ ጌታ ያዘዘኝን አውቃለሁ፣ እናም በዚ ህም እደሰታለሁ። በራሴ ᵐአልኮራም፣ ነገር ግን ጌታ እኔን ባዘዘኝ በዚያ እኮራ ለሁ፤ አዎን፣ ይህም ምናልባት ጥቂት ነፍ ሳትን ወደ ንስሃው በማምጣት በእግዚአብ ሔር እጅ መሳሪያ እሆን ዘንድ በዚህ እመካ ለሁ፤ እናም ይህም የእኔ ደስታ ነው።

፲፩ እናም እነሆ፣ ብዙዎቹ ወንድሞቼ በእ ውነት ንስሃ መግባታቸውን፣ እና ወደጌታ አምላካቸው መምጣታቸውን በተመለከ ትኩ ጊዜ፣ ከዚያም ነው ነፍሴ በደስታ የተ ሞላችው፤ በዚያም ᵐጌታ ምን እንዳደረገ ልኝ፣ አዎን፣ ፀሎቴንም እንኳን እንደሰ ማልኝ ለማስታወስ እችላለሁ፤ አዎን በዚ ያም የምህረት ክንዶቹ በእኔ ላይ መዘርጋ ታቸውንም አስታውሳለሁ።

፲፪ አዎን፣ እናም ደግሞ የአባቶቻችንን ምርኮ አስታውሳለሁ፤ ᵐጌታ ከባርነት እን ደለቀቃቸው በእርግጥ አውቃለሁ፣ እናም በዚህም ቤተክርስቲያኗን አቋቁሟል፤ አዎን፣ ጌታ እግዚአብሔር፣ የአብርሃም አምላክ፣ የይስሀቅ አምላክ፣ እንዲሁም የያዕቆብ አምላክ ከባርነት ለቋቸዋል።

፲፫ አዎን፣ የአባቶቻችንን ምርኮ ሁልጊ ዜም አስታውሳለሁ፤ እናም ከግብፃውያን እጅ ᵐያስለቀቃቸው አምላክ ከባርነት እነ ርሱንም አስለቅቋል።

፲፬ አዎን፣ እናም ይኸው አምላክ ቤተክር ስቲያኗን በመካከላቸው አቋቁሟል፤ አዎን፣ ይኸውም አምላክ ቃሉን ለህዝቡ እንድሰብክ በቅዱሱ ጥሪው ጠራኝ፤ እናም ብዙ ድልም ሰጠኝ፤ በዚህም ᵐደስታዬ የተሞላ ነው።

፲፭ ነገር ግን በራሴ ስኬታማነት ብቻ አል ደሰትም፣ ነገር ግን በኔፊ ምድር በነበሩት ወንድሞቼ ᵐስኬታማነት ደስታዬ ይበልጥ ሙሉ ነው።

፲፮ እነሆ፣ እነርሱ እጅግ ሰሩም፣ በርካታ ፍሬን አምጥተዋልም፤ እናም ደመወዛቸው እንዴት ታላቅ ይሆናል!

፲፯ አሁን፣ የእነዚህን የወንድሞቼን ስኬት ባሰብኩ ጊዜ ነፍሴ ከስጋዬ እንደተለየች ያህል ትወሰዳለች፣ በመሆኑም ደስታዬም ታላቅ ነው።

፲፰ እናም አሁን እግዚአብሔር ለወንድ ሞቼ በእግዚአብሔር መንግስት እንዲቀ መጡ ለእነርሱ ይፈቀድላቸው፤ አዎን፣ እናም ደግሞ የስራቸው ውጤት የሆኑት ሁሉ ከእንግዲህ እንዳይሄዱባቸው፤ ነገር ግን ለዘለዓለም እርሱን ያወድሱት። እናም እኔ እንደተናገርኩት እንደቃሌም እንዲ ሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን። አሜን።

ምዕራፍ ፴

ፀረ ክርስቶስ የሆነው ቆሪሆር፣ በክርስ

፭ ሀ ፪ ኔፊ ፪፡፲፰፡ ፳፯፤
ሞሮኒ ፯፡፲፭–፲፱።
ቅ.መ.መ. የመለየት ስጦታ።
ለ ቅ.መ.መ. ህሊና።
፰ ሀ ፪ ኔፊ ፳፱፡፲፪።
ለ አልማ ፲፪፡፱–፲፭።
ሐ ት.እና ቃ. ፣፡፣፡፲፭።
፱ ሀ አልማ ፳፯፡፲፪።
፲ ሀ ሞዛያ ፳፯፡፲፭–፴፭።
፲፭ ሀ ሞዛያ ፳፡፲፯–፳፭፤
አልማ ፭፡፲–፭።
፲፪ ሀ ዘፀአ. ፲፡፡–፴–፴፭።
፲፫ ሀ ት.እና ቃ. ፲፰፡፲፡–፲፯።
፲፡ ሀ አልማ ፲፯፡፭–፡።

ቶስ፣ በኃጢያት ክፍያው እና በትንቢት መንፈስ ተሳለቀ—እግዚአብሔር እንደ ሌለ፣ የሰው ልጅ መውደቅ እንደሌለ፣ ለኃጢያትም ቅጣት እንደሌለና፣ ክርስቶስ እንደሌለ አስተማረ—አልማ ክርስቶስ እንደሚመጣና ሁሉም ነገር እግዚአብሔር መኖሩን እንደሚያመለክት መሰከረ—ቆሪሆር ምልክትን ፈለገና ዲዳ ሆነ—ዲያብሎስ ለቆሪሆር እንደመልአክ ታይቶት እናም ምን ማለት እንዳለበት አስተምሮት ነበር—ቆሪሆር ተረገጠ፣ እናም ሞተ። ከ፳፪–፳፱ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እነሆ አሁን እንዲህ ሆነ ᵐየአሞን ህዝብ በኢየርሾን ምድር ከተቋቋሙ በኋላ፣ አዎን እናም ደግሞ ላማናውያን ከምድሪቱ ᵃከተባረሩ እናም የሞቱባቸው በነዋሪው ከተቀበሩ በኋላ—

፪ አሁን የሞቱባቸው ቁጥራቸው እጅግ ብዙ ስለነበር አልተቆጠሩም፤ ከኔፋውያን የሞቱትንም ለመቁጠር አይቻሉም ነበር—ነገር ግን እንዲህ ሆነ ሙታኖቻቸውን ከቀበሩ በኋላ፣ እናም ደግሞ ከየማቸውና፣ ከሀዘናቸው፣ እንዲሁም ከፀለዩበት ቀናት በኋላ (እናም ይህም በኔፊ ህዝብ ላይ በአስራ ስድስተኛው የመሣፍንት አገዛዝ ዘመን ነበር) በምድሪቱ ላይ ሁሉ የማያቋርጥ ሰላም መሆን ጀመረ።

፫ አዎን፣ እናም ህዝቡ የጌታን ትዕዛዛት ለመጠበቅ ጥረት አደረጉ፤ እናም በሙሴ ህግ መሰረትም ᵐየእግዚአብሔርን ስርዓቶች ለመፈፀም የሚተጉ ነበሩ፤ የሙሴን ህግም እስኪፈፀም ᵃለመጠበቅ ተምረው ነበርና።

፬ እናም ህዝቡ በኔፊ ህዝብ ላይ በኔፊ ህዝቦች ላይ በነገሱበት በአስራ ስድስተኛው የመሳፍንት ዘመን ውስጥ ሁሉ ምንም ሁከት አልነበረባቸውም።

፭ እናም እንዲህ ሆነ በአስራ ሰባተኛው የመሣፍንት የንግስ ዘመንም መጀመሪያም ላይ የማያቋርጥ ሰላም ነበር።

፮ ነገር ግን እንዲህ ሆነ በአስራ ሰባተኛው ዓመት በስተመጨረሻ አንድ ሰው ወደ ዛራሔምላ ምድር መጣ፣ እርሱም ᵐፀረ ክርስቶስ ነበር፤ እናም ስለክርስቶስ መምጣት በነቢያቱ የተነገሩትን ትንቢቶች በመቃረን መስበክ ጀመረ።

፯ እንግዲህ የሰዎችን ᵐእምነት የሚፃረር ህግ አልነበረም፤ ምክንያቱም ሰዎችን እኩል የማያደርግ ህግ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ፈፅሞ የተቃረነ ነውና።

፰ ስለዚህ ቅዱስ መጽሐፍ እንዲህ ይላልና፥ የምታመልኩትን ዛሬ ᵐምረጡ።

፱ እንግዲህ ሰው እግዚአብሔርን ለማገልገል ከፈለገ ይህ ልዩ መብቱ ነው፤ ወይም፣ በእግዚአብሔር ካመነ እርሱን ማገልገል መብቱ ነው፤ ነገር ግን በእርሱ ካላመነ እርሱን ለመቅጣት ምንም ዓይነት ህግ የለም።

፲ ነገር ግን የሚገድል ከሆነ ᵐበሞት ይቀጣል፤ እናም ዘራፊ ከሆነም ደግሞ ይቀጣል፤ የሚሰርቅ ከሆነም ደግሞ ይቀጣል፤ እናም ዝሙትን ከፈፀመ ይቀጣል፤ አዎን ለዚህ ሁሉ ኃጢአቶች ተቀጥተዋል።

፲፩ ሰው እንደወንጀሉ የሚዳኝበት ህግ ነበርና። ይሁን እንጂ የሰውን እምነት የሚፃረር ህግ አልነበረም፤ ስለዚህ ሰው ባጠፋበት ብቻ የሚቀጣበትም ህግ ነበር፣ ስለዚህ ሰዎች ሁሉ ᵐእኩል አቋም ነበራቸው።

፲፪ እናም ይህ ቆሪሆር የሚባለው ፀረ ክርስቶስ፣ (እናም ህጉ በእርሱ ላይ መስራት የማይችለው) ክርስቶስ እንደሌለ ለህዝቡ ማስተማር ጀመረ። እናም እንዲህም በማለት ሰበከ፥

፲፫ አቤቱ በሞኝና በከንቱ ተስፋ የታሰራችሁ፣ ለምን ራሳችሁን በከንቱ ነገሮች ትገድባላችሁ? ክርስቶስንስ ለምንስ ትጠ

ᵃ ፩ ሆ አልማ ፳፯፡ ፳፭–፳፯።
ᵐ ቅ.መ.መ. አንቲ-ኔፊ-ሌሂ።
ᵃ ለ አልማ ፳፰፡ ፩–፫።
ᵐ ፫ ሆ ቅ.መ.መ. የሙሴ ህግ።
ᵃ ለ ፪ ኔፊ ፳፭፡ ፳፱–፳፯፤ አልማ ፳፭፡ ፲፭።
ᵐ ፯ ሆ ቅ.መ.መ. የክርስቶስ ተቃዋሚ።
ᵐ ፯ ሆ አልማ ፩፡ ፲፯።
ᵐ ፰ ሆ ኢ.ያ. ፳፬፡ ፲፭።
ᵐ ፱ ሆ አልማ ፳፱፡ ፴፱–፴፪።
ᵐ ፲ ሆ ቅ.መ.መ. ነጻ ምርጫ።
ᵐ ፲ ሆ ቅ.መ.መ. የሞት ቅጣት።
ᵐ ፲፩ ሆ ሞዛያ ፳፱፡ ፴፪።

ብቃላችሁ? ምክንያቱም ማንም ሰው የሚ መጣውን ማንኛውንም ነገር ማወቅ አይ ችልም።

፲፬ እነሆ እነዚህ ትንቢት ብላችሁ የም ትጠሩአቸው፣ በቅዱሳን ነቢያት ሲወርዱ መጥተዋል የምትሏቸው ነገሮች፣ እነሆ እነ ርሱ የአባቶቻችሁ ከንቱ ወግ ናቸው።

፲፭ እርግጠኝነታቸውን እንዴት ታውቃ ላችሁ? እነሆ ᐟያላያችኋቸውን ነገሮች ለማ ወቅ አትችሉም፤ ስለዚህ ክርስቶስ እንደ ሚኖርም ለማወቅ አትችሉም።

፲፮ ወደፊትም ትመልከታላችሁ፣ እናም የኃጢአታችሁን ስርየት አየን ትላላችሁ። ነገር ግን እነሆ፣ ይህ የአዕምሮ እብደት ውጤት ነው፤ እናም ይህ የአዕምሮአችሁ እብደት የመጣው እናንተ ወዳልሆኑ እም ነት በሚመራችሁ በአባቶቻችሁ ወግ ምክ ንያት ነው።

፲፯ እናም ለሰው ልጆች የኃጢያት ክፍ ያም መሆን እንደማይችል፤ ነገር ግን ማን ኛውም ሰው በዚህ ህይወት እድሉን የሚወ ስነው እራሱ በሚያደርገው ነው እያለ እንደ ነዚህ ያሉ ብዙ ነገሮችን ተናገራቸው፤ ስለ ዚህ እያንዳንዱ ሰው በተሰጥኦው ይበለፅ ጋል፣ እያንዳንዱም ሰው በጉልበቱ ያሸ ንፋል፤ እናም ማንም ሰው ያደርገው የነበ ረው ሁሉ ወንጀል አልነበረም።

፲፰ እናም እርሱ ህዝቡን ሰበከ፣ የብዙዎ ችንም ልብ አሳተ፣ በኃጢአታቸው እራ ሳቸውን ቀና እንዲያደርጉ አደረገ፤ አዎን ብዙ ሴቶችንና ደግሞ ወንዶችን ዝሙት እንዲፈፅሙ አደረገ—ሰው ሲሞት፣ በእ ዚያም ሁሉም ነገር እንደተፈጸመ ነግሯ ቸዋል።

፲፱ እንግዲህ ይህ ሰው በአንድ ወቅት የላ ማናውያን ህዝብ በነበሩት በአሞን ህዝቦች መካከል እነዚህን ነገሮች ለመስበክ ወደ ኢየርሾን ምድር ሄደ።

፳ ነገር ግን እነሆ እነርሱ ከአብዛኞቹ ኔፋ ውያን የበለጠ ብልህ ነበሩ፤ ምክንያቱም እርሱን ወሰዱትና፣ አሰሩት፣ እናም ህዝብ ላይ ሊቀ ካህን ወደሆነው ወደ አሞን ዘንድ ወሰዱት።

፳፩ እናም እንዲህ ሆነ እርሱም ከምድ ሪቱ ተወስዶ እንዲወጣ አደረገ። እናም ወደ ጌዴዎን ምድር መጣና፣ ደግሞ ለህ ዝቡ መስበክ ጀመረ፣ እናም በዚያ ብዙ ድል አላገኘም ነበር፣ ምክንያቱም እርሱ ተወሰ ደና ታሰረ፣ እናም ወደ ምድሪቱ ሊቀ ካህ ንና ደግሞ በዋናው ዳኛ ፊት ቀርቧልና።

፳፪ እናም እንዲህ ሆነ ሊቀ ካህኑም እን ዲህ አለው፥ የጌታን መንገድ ለማሳት ለምን ትሄዳለህ? ይህንን ህዝብ ደስታውን ለማቋ ረጥ ለምን ክርስቶስ የለም ብለህ ታስተምራ ለህ? ከቅዱሳን ነቢያት ትንቢት ሁሉ ተቃ ራኒ የሆነውንስ ለምንስ ትናገራለህ?

፳፫ እንግዲህ የሊቀ ካህኑም ስም ጊዶና ነበር። እናም ቆሪሆር እንዲህ አለው፥ ከንቱ የሆነውን የአባቶችህን ወግ አላስተምርም፣ እናም ያለአግባብ ኃይላቸውንና ሥልጣና ቸውን በእነርሱ ላይ ለማድረግ፣ እራሳቸ ውንም ቀና እንዳያደርጉ ነገር ግን በቃላቶ ችህ መጥፎ እንዲሰማቸው፣ ደንቆሮ ለማ ድረግ፣ ይህንን ህዝብ ከንቱ በሆነው ስርዓ ትና በጥንት ካህናት የተመሰረተውን አሰ ራር ለማሰር ይህንን ህዝብ አላስተምርም።

፳፬ አንተም ይህ ህዝብ ነፃ ነው ብለሃል። እነሆ፣ እነርሱ በባርነት ናቸው እላለሁ። የጥንት ትንቢቶች እውነት ናቸው ብለ ሃል። እነሆ፣ እነርሱ እውነት መሆናቸውን አታውቅም እላለሁ።

፳፭ በወላጆቻቸው መሳሳት ምክንያት ይህ ህዝብ ጥፋተኛና የወደቀ ነው ትላላችሁ። እነሆ፣ ልጅ በወላጆቹ ምክንያት ጥፋተኛ አይሆንም እላለሁ።

፳፮ እናም ደግሞ ክርስቶስ ይመጣል ብለ ሃል። ነገር ግን እነሆ፣ ክርስቶስ እንደሚኖር አታውቅም እላለሁ። እናም ደግሞ አንተ ለዓለም ᐟኃጢያት ይሞታል ብለሃል—

፳፯ እናም ይህን ህዝብ ከንቱ በሆነው በአ ባቶች ወግና እንደ ፍላጎትህ መሰረት እን ደዚህ ትመራለህ፤ እናም በባርነት እንዳ

ሉም፣ በእጆቻቸው በሰሩትም ራስህን ታን ደላቅቅበት ዘንድ፣ በድፍረትም ለመመ ልከት እንዳይደፍሩና፣ በልዩ መብቶቻቸ ውና በዕድላቸውም ለመደሰት እንዳይደፍሩ ተገዢ ታደርጋቸዋለህ።

፳፯ አዎን፣ እንደራሳቸው ፍላጎት ያሰራ ቸውን፣ እና በወጎቻቸውና ህልሞቻቸው፣ ቅዠታቸውና፣ ራዕዮቻቸው፣ እናም የማ ስመሰል ሚስጥሮቻቸው እንዲያምኑ ያደ ረጓቸውን ካህናቶቻቸውን እናሳዝናቸዋ ለን ብለው ይፈራሉ፣ እናም ያንኑ ማድረግ ነበረባቸውና፣ እንደቃሎቻቸው የማያደ ርጉም ከሆነ እነርሱ አምላክ ብለው ያሉ ትን—አንድ ያልታወቀን፣ እስከዛሬ ያል ታየን፣ ወይንም እስከዛሬ ያልታወቀን አም ላክ እናሳዝናለን ይላሉ።

፳፱ እንግዲህ ሊቀ ካህኑና ዋናው ዳኛ የልቡን ጠጣርነት በተመለከቱ ጊዜ፣ አዎን በእግዚአብሔር ላይ መሳደቡን በተመለ ከቱ ጊዜ፣ ለቃሉ ምንም መልስ አልሰ ጡም፤ ነገር ግን እንዲታሰር አደረጉ፤ እናም ለሹማምንቶቹ አስረከቡት፣ እናም ከዋናው ዳኛ፣ በምድሪቱ ላይ ሁሉ ገዢ ከነበረው ከአልማ ፊት ይቀርብ ዘንድ ወደ ዛራሔምላ ምድር ላኩት።

፴ እናም እንዲህ ሆነ ከዋናው ዳኛና ከአ ልማ ፊት በቀረበ ጊዜ፣ በጌዴዎን ምድርም ያደርግ እንደነበረው ማድረጉን ቀጠለ፣ አዎን፣ [ሀ]የእግዚአብሔርንም ስም በከንቱ ማንሳቱን ቀጠለ።

፴፩ እናም በአልማ ፊት [ለ]ጮክ ብሎ ለመ ናገር ተነሳ፣ እናም በህዝቡም ድካም ለመ ንደላቀቅ፣ በከንቱው የአባቶቻቸው ወግ ይመሯቸዋል በማለት ካህናቶቹንና መም ህራንን በመሳደብ ይከሳቸው ጀመር።

፴፪ እንግዲህ አልማ እንዲህ አለው፥ በዚህ ህዝብ ስራ አለመንደላቀቃችንን ታውቃለህ፤ እነሆም ከመሣፍንት አገዛዝ ጀምሮ ምንም እንኳን በምድሪቱ ዙሪያ ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል ለህዝቡ ለማ ወጅ የተጓዝኩ ቢሆንም እስካሁን ድረስ ራሴን ለመርዳት ሰርቼአለሁ።

፴፫ እናም በቤተክርስቲያን ውስጥ ብዙ ስራዎችን የሰራሁ ቢሆንም ለስራዬ አንድ [ሐ]ሰኒን እንኳን አልተቀበልኩም፤ ከፍርድ ወንበሩ በስተቀር ወንድሞቼም አልተቀበ ሉም፤ እናም በዚያም የተቀበልነው በህጉ መሰረት ለጊዜአችን ነበር።

፴፬ እናም አሁን በቤተክርስቲያኗ ለሰራ ንበት ምንም የማናገኝ ከሆነ በወንድሞቻ ችን [ሀ]ደስታ ሐሴት እናደርግ ዘንድ በቤተ ክርስቲያኗ እውነትን ለማወጅ ማገልገላችን እኛን ምን ይጠቅመናል?

፴፭ አንተ ራስህ እኛ ምንም ጥቅም እንዳ ላገኘን ባወቅህ ጊዜ ከህዝቡ ጥቅም እንድና ገኝ ነው የምንሰብከው ለምን አልህ? እናም አሁን በህዝቡ ልብ ውስጥ ደስታን እንደ ሚፈጥር አድርገን ይህንን ህዝብ እንዳታ ለልን ታምናለህን?

፴፮ እናም ቆሪሆር አዎን በማለት መለሰ።

፴፯ እናም አልማ እንዲህ አለ፥ እግዚአ ብሔር እንዳለ ታምናለህን?

፴፰ እናም አላምንም ሲል መለሰ።

፴፱ እንግዲህ አልማ እንዲህ አለው፥ በድጋሚ እግዚአብሔር እንዳለ ትክዳ ለህን፣ እናም ደግሞ ክርስቶስን ትክዳለ ህን? እነሆም እንዲህ እልሃለሁ፣ እግዚአ ብሔር እንዳለና ደግሞ ክርስቶስ እንደሚ መጣ አውቃለሁ።

፴ እናም አሁን [ሀ]እግዚአብሔር እንደሌለ፣ ክርስቶስም እንደማይመጣ ምን ማረጋገጫ አለህ? ከቃላትህ በስተቀር ምንም ማረጋ ገጫ የለህም እላለሁ።

፴፩ ነገር ግን፣ እነሆ፣ እነዚህ ነገሮች እው ነት ለመሆናቸው [ሀ]ለምስክርነት ሁሉም ነገር አሉኝ፤ እናም አንተ ደግሞ እውነት ለመሆ ናቸው ሁሉም ነገሮች ለምስክርነት አሉህ፤ እናም አንተ እነዚህን ትክዳለህን? እነዚህ ነገሮች እውነት መሆናቸውን ታምናለህን?

፴፪ እነሆ፣ ማመንህን አውቃለሁ፣ ነገር

፴ ሀ ቅ.መ.መ. መስደብ።
፴፩ ሀ ሉ. ፲፫፡ ፳፪።
፴፪ ሀ አልማ ፲፩፡ ፲፡
፴፬ ሀ ቅ.መ.መ. ደስታ።
፴ ሀ መዝ. ፲፬፡ ፩።
፴፩ ሀ ቅ.መ.መ. ምስክር።

ግን አንተ ለውሸት መንፈስ ተገዝ ሆነሃል፣ እናም በውስጥህ ሥፍራ እንዳይኖረው የእ ግዚአብሔርን መንፈስ ክደሃል፤ ነገር ግን ዲያብሎስ በአንተ ላይ ስልጣን አለው፣ እናም የእግዚአብሔርን ልጆች ያጠፋበት ዘንድ በዕቅዱ በአንተ ላይ ገዝ ሆኗል።

፴፫ እናም አሁን ቆሪሆር ለአልማ እንዲህ አለው፡ እግዚአብሔር መኖሩን ለማመን እችል ዘንድ ለእኔ ᵐምልክትን የምታሳየኝ ከሆነ፡ አዎን፣ ኃይል እንዳለው አሳየኝ፣ እናም በቃልህ እውነተኛነት አምናለሁ።

፴፬ ነገር ግን አልማ እንዲህ አለው፡ በቂ ምልክት አግኝተሃል፣ አምላክህን ትፈ ትናለህን? ᵐየወንድሞችህ ሁሉና፣ ደግሞ የቅዱሳን ነቢያት ምስክርነትን ባገኘህ ጊዜ ምልክት አሳዩኝ ትላለህን? ቅዱሳት መጻሕ ፍት በፊትህ ቀርበውልሃል፣ አዎን፣ እናም ᵃሁሉም ነገር እግዚአብሔር መኖሩን ያመ ለክታሉ፣ አዎን፣ ሐምድርም እንኳን፣ እናም ሁሉም በምድር ገፅ ላይ ያሉት ነገ ሮች በሙሉ፤ አዎን እናም የምድር ᵐእንቅ ስቃሴ፣ አዎን፣ እናም ደግሞ በተለመደው ሁኔታ የሚንቀሳቀሱት ᵐፕላኔቶች ታላቅ ፈጣሪ እንዳለ ያመለክታሉ።

፴፭ እናም የዚህን ህዝብ ልብ በማሳሳት እግዚአብሔር የለም ብለህ ለመመስከር ትሄዳለህን? እናም የእነዚህን ሁሉ ምስክ ርነት ትክዳለህን? እንዲህም አለ፡ አዎን፣ ምልክትን ካላሳየኸኝ እክዳለሁ።

፴፮ እናም እንግዲህ እንዲህ ሆነ አልማ እንዲህ አለው፡ እነሆ፣ በልብህ ጠጣርነት፣ አዎን፣ ነፍስህም እንድትጠፋ ዘንድ የእው ነትን መንፈስ ስለምትቃወም አዝኜአለሁ።

፴፯ ነገር ግን እነሆ፣ በውሸታሙና በሚ ሸነግለው ቃልህ ብዙ ነፍሳትን ወደጥፋት ከማምጣት ይልቅ ነፍስህ ብትጠፋ ᵐይሻ ላል፤ ስለዚህ በድጋሚ ከካድህ እነሆ እግ ዚአብሔር ይመታሃል፣ ደንቆሮም ትሆና ለህ፤ ከእንግዲህም አፍህን ለመክፈት አት ችልም፣ ከእንግዲህም ይህንን ህዝብ አታ ታልልም።

፴፰ እንግዲህ ቆሪሆር እንዲህ አለው፡ የእግዚአብሔርን መኖር አልክድም፣ ነገር ግን እግዚአብሔር እንዳለ አላምንም፤ እናም ደግሞ እንዲህ እላለሁ፡ እግዚአብ ሔር እንዳለም አንተ አታውቅም፤ እናም ምልክትን ካላሳየኸኝ አላምንም።

፴፱ እንግዲህ አልማ እንዲህ አለው፡ ይህን ለአንተ በቃሌ መሰረት ᵐዲዳ እንድ ትሆን ለምልክት እሰጥሃለሁ፤ እናም በእ ግዚአብሔር ስም፣ ከእንግዲህ እንዳትናገር ዲዳ እንድትሆን ይህን እላለሁ።

፴ እንግዲህ አልማ እነዚህን ቃላት በተና ገረ ጊዜ፣ በአልማ ቃል መሰረትም ለመና ገር እንዳይችል ቆሪሆር ዲዳ ሆነ።

፴፩ እናም ዋናው ዳኛ ይህን በተመለከተ ጊዜ፣ ለቆሪሆር እንዲህ በማለት ፃፈለት፡ በእግዚአብሔር ኃይል አምነህልን? አልማ በማን ላይ ምልክቱን እንዲያሳይ ፈልገህ ነበር? ለአንተ ምልክቱን ለማሳየት ሌሎችን እንዲያሰቃይ ትፈልጋለህን? እነሆ፣ ምልክ ትን አሳይቶሀል፤ እናም አሁን ከዚህ በላይ ትከራከራለህን?

፴፪ እናም ቆሪሆር እጁን አነሳ፣ እንዲ ህም በማለት ፃፈ፡ ዲዳ መሆኔን አውቃ ለሁ፣ ምክንያቱም ለመናገር አልቻልኩም፤ እናም ከእግዚአብሔር ኃይል በቀር ማንም በእኔ ላይ ይህን ማምጣት እንደማይችል አውቃለሁ፤ አዎን፣ ሁል ጊዜም እግዚአ ብሔር እንዳለም ᵐአውቅ ነበር።

፴፫ ነገር ግን እነሆ፣ ዲያብሎስ ᵐአሳተኝ፤ ምክንያቱም እርሱ በመልአክ አምሳል ᵃታየኝ፣ እናም እንዲህ አለኝ፡ ሂድና ህዝቡ ሁሉ ወደ ማይታወቀው አምላክ በተሳሳተው መንገድ ሄደዋልና መልሳቸው። እናም እን ዲህ አለኝ፡ እግዚአብሔር ᵃየለም፤ አዎን፣

፴፫ ᵐ ሆ ያዕቆ. ፯፡ ፲፫–፳፭፤ ት. እና ቃ. ፵፯፡ ፳–፳፱። ቅ.መ.መ. ምልክት።
፴፬ ᵐ ሞዛያ ፲፫፡ ፴፫–፴፭። ᵃ መዝ. ፲፱፡ ፩፤
ት. እና ቃ. ፹፰፡ ፳፯። ᵃ ሐ ኢዮብ ፲፪፡ ፯–፲። ᵐ ሔለ. ፲፪፡ ፲፩–፲፭። ᵃ ሥ ሙሴ ፮፡ ፳፫።
፴፯ ᵐ ᵃ ኔፊ ፬፡ ፲፫።
፴፱ ᵐ ᵃ ዘና ፲፫፡ ፳። ᵐ ᵃ አልማ ፴፡ ፴፪።
፴፫ ᵐ ᵃ ያዕቆ. ፯፡ ፲፬። ᵃ ᵃ ቆሮ. ፲፩፡ ፲፬፤ ᵃ ኔፊ ፱፡ ፱። ᵃ መዝ. ፲፡ ፬።

ማለት ያለብኝንም አስተማረኝ። ቃሉንም አስተማርኩኝ፤ እናም መለስጋዊ አዕምሮ የሚያስደስቱ በመሆናቸው አስተማርኳ ቸው፤ እናም አጥጋቢ ውጤት እስከማገኝ ድረስ አስተማርኳቸው፣ እንዲህም ሆኖ በእርግጥም እውነት መሆናቸውንም አመ ንኩኝ፤ ይህንንም ታላቅ እርግማን በራሴ ላይ እስከማመጣው ድረስ እውነትን የተ ቃወምኩት ለዚህም ነው።

፶፬ እንግዲህ እርሱ ይህንን በተናገረ ጊዜ፣ እርግማኑ ከእርሱ እንዲወሰድ አልማ ወደ እግዚአብሔር እንዲፀልይ ለመነው።

፶፭ ነገር ግን አልማ እንዲህ አለው፡ ይህ እርግማን ከአንተ ከተወሰደ በድጋሚ የህ ዝቡን ልብ ወደ ስህተት ትመራለህ፤ ስለ ዚህ፣ ጌታ እስከፈቀደ ድረስ ይህ በአንተ ላይ ይሆናል።

፶፮ እናም እንዲህ ሆነ እርግማኑ ከቆሪሆር አልተወሰደም፤ ነገር ግን እርሱ ወደውጪ ተጣለና፣ ከቤት ወደ ቤት ምግብ በመለ መን ተዘዋወረ።

፶፯ እንግዲህ በቆሪሆር ላይ የሆነው ወዲ ያውኑ በምድሪቱ ሁሉ ተወራ፤ አዎን፣ አዋጁ በቆሪሆር ቃል ለሚያምኑት በፍጥ ነት ንስሃ እንዲገቡ አለበለዚያ ተመሳሳዩ ፍርድ በእነርሱ ላይ እንደሚመጣ በማወጅ አዋጁ ለምድሪቱ ነዋሪዎች ሁሉ በዋናው ዳኛ ተላከ።

፶፰ እናም እንዲህ ሆነ ሁሉም ስለቆሪሆ ርን ኃጢያት አመኑ፤ ስለዚህ ሁሉም በድ ጋሚ ወደ ጌታ ተለወጡ፣ እናም ይህም በቆሪሆር መተላለፍ ስለነበረው ማብቂያ ሆነ። ቆሪሆርም እራሱን ለመርዳት ከቤት ቤት በምግብ ልመና ዞረ።

፶፱ እናም እንዲህ ሆነ በህዝቡ፣ አዎን ከኔፋዉያን መካከል እራሳቸውን የለዩትና ዞራማውያን ብለው የጠሩት፣ ዞራም ተብሎ በሚጠራው ሰው በተመሩት መካከል በሄደ ጊዜ—እናም በእነርሱ መካከል በሄደ ጊዜ፣ እነሆ እስከሚሞት ድረስ ተረማመዱበትም ተረጋገጡበት።

፷ እናም እኛ የጌታን መንገድ የሚያሰተ ውን የእርሱን መጨረሻ እንመለከታለን፣ እንደዚህም ᵐዲያብሎስ በመጨረሻው ቀን ልጆቹን ᵃእንደማይደግፍ ነገር ግን በፍጥ ነት ᵇወደሲኦል እንደሚጎትታቸው እንመ ለከታለን።

ምዕራፍ ፴፭

አልማ ኃይማኖታቸውን የካዱትን ዞራማ ውያን ለመመለስ ተልዕኮውን መራ—ዞራማውያን ክርስቶስን ካዱ፤ በውሸት የምርጫ ሀሳብ አመኑ፣ እናም በተወሰነ ፀሎት አመለኩ—አገልጋዮች በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ—ስቃያቸው በክርስቶስ ደስታ ተውጠዋል። በ፳፱ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ ቆሪሆር ከሞተ በኋላ፣ ዞራማውያን የጌታ ጎዳናን መበከላቸውን እናም መሪያቸው የነበረው ዞራም የሰዎ ችን ልብ ᵐጣኦትን ለማምለክ ᵃእንዲያጎነ ብስ መምራቱን አልማ ወሬውን በመስማቱ ልቡ በህዝቡ ኃጢያት ምክንያት ᵇመታ ወክ ጀመረ።

፪ በህዝቡ መካከል ያለውን ክፋት ማወቅ ለአልማ ታላቅ ᵐሀዘን ነበር፤ ስለዚህ ልቡም ዞራማውያን ከኔፋውያን በመለየታቸው እጅግ አዘነ።

፫ አሁን በዛራሔምላ በስተምስራቅ በባህሩ ዳርቻ፣ በኢየርሾን ምድር በስተደ ቡብ፣ ላማናውያን በሞሉበት በምድረበዳው በደቡብ ዳርቻ አንቲዮኑም ብለው በሚጠ ሩት ስፍራ ውስጥ ዞራማውያን እራሳቸውን በአንድ ላይ ሰበሰቡ።

፬ አሁን ዞራማውያን ከላማናውያን ጋር የህብረት ስምምነት ያደርጋሉ፣ እናም

፶፫ መ ቅ.መ.መ. ስጋዊ።
፶፮ ሀ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
ለ አልማ ፫፡ ፳፯—፳፯፤ ፭፡ ፶፭—፶፭፤ ት.እና ቃ. ፳፱፡ ፶፭።
ሐ ቅ.መ.መ. ሲያል።
፴፭ ፩ ሀ ፪ ኔፊ ፱፡ ፴፯። ቅ.መ.መ. ጣኦት አምላኪ።
ለ ዘፀአ. ፳፡ ፭፤ ሞዛያ ፲፫፡ ፲፫።
ሐ አልማ ፴፭፡ ፲፭። ፪ ሀ ሞዛያ ፳፯፡ ፫፤ ፫ ኔፊ ፲፯፡ ፲ፀ፤ ሙሴ ፯፡ ፶፭።

ይህም ለኔፋውያን የታላቅ ጥፋት መንስኤ ይህናል በማለት ኔፋውያን እጅግ ፈሩ።

፭ እናም አሁን፣ [ሀ]የቃሉ [ለ]መሰበክ ህዝቡ ትክክለኛውን እንዲሰራ [ሐ]የሚመራ ታላቅ ዝንባሌ ስላለው—አዎን፣ ይህም ከጎራዴ፣ ወይም ከሚሆንባቸው ማንኛውም ነገር፣ የበለጠ በአዕምሮአቸው ላይ ውጤት ይኖረዋል—ስለዚህ አልማ ኃያል ውጤት ያለውን የእግዚአብሔር ቃል በጎነት መሞከራቸው አስፈላጊነቱን አሰበ።

፮ ስለዚህ አሞንን፣ አሮንንና፣ ኦምነርን ወሰደ፤ እናም ሂሚኒን በዛራሔምላ ቤተክርስቲያን ተወው፤ ነገር ግን ቀዳሚዎቹ ሶስቱን ከእርሱ ጋር ወሰዳቸውና፣ ደግሞ በሜሌቅ የነበሩትን አሙሌቅንና፣ እና ዚኤዝሮምን፣ ደግሞም ሁለት ወንድ ልጆቹን ወሰደ።

፯ እንግዲህ [ሀ]ሔለማን የሚባለውን ትልቁን ልጁን ከእርሱ ጋር አልወሰደውም፤ ነገር ግን ከእርሱ ጋር የወሰዳቸው ስማቸው ሺብሎንና፣ ቆሪያንቶን ይባላሉ፤ እናም ቃሉን [ለ]በዞራማውያን መካከል ለመስበክ ከእርሱ ጋር የሄዱት ስማቸው እነዚህ ናቸው።

፰ እናም ዞራማውያን ከኔፋውያን [ሀ]የተገ ነጠሉ ነበሩ፤ ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል ተሰብኮላቸው ነበር።

፱ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት እናም ስርዓቶቹ በሙሴ ህግ መሰረት ባለመጠበቃቸው በታላቅ ስህተት ውስጥ [ሀ]ወደቁ።

፲ ወደፈተናው እንዳይገቡ ዕለት ዕለትም እግዚአብሔርን በመለመን በፀሎታቸው የሚቀጥሉበትን የቤተክርስቲያኗን ስርዓት አላከበሩም።

፲፩ አዎን፣ በአጠቃላይ፣ የጌታን መንገድ በብዙ ሁኔታዎች አጣመዋል፤ ስለዚህ፣ ለዚህ ምክንያት አልማና ወንድሞቹ ለእነርሱ ቃሉን ለመስበክ ወደምድሪቱ ሄደዋል።

፲፪ እንግዲህ፣ ወደምድሪቱ በመጡ ጊዜ፣ እነሆ፣ ለመገረማቸው ዞራማውያን ምኩራብን ሠርተው አገኙአቸው፣ እናም የጌታቀን ብለው በሚጠሩት ቀንም በሳምንት አንድ ቀን በአንድ ላይ እራሳቸውን ይሰበስባሉ፤ እናም አልማና ወንድሞቹ አይተውት በማያውቁት ሁኔታ ያመልካሉ፤

፲፫ በምኩራባቸው ለመቆሚያነት ከጭን ቅላት በላይ ከፍ ያለን ቦታ በመሀከሉ ሰርተው ነበር፤ እናም ጫፉም ላይ ለመግባት የሚያስችለው አንድን ሰው ብቻ ነበር።

፲፬ ስለዚህ፣ [ሀ]ማምለክ የፈለገ መሄድና በጫፉ ላይ መቆም አለበት፤ እናም ወደ ሰማይ እጁን በመዘርጋት፣ እናም በኃይል እንዲህ በማለት ይጮሃል፥

፲፭ ቅዱስ፣ ቅዱስ እግዚአብሔር፤ አንተ አምላክ መሆንህን እናምናለን፣ ቅዱስ መሆንህንና፣ አንተ መንፈስ እንደነበርክ፣ መንፈስም እንደሆንክ፣ እናም ለዘለዓለም መንፈስ እንደምትሆን እናማንለን።

፲፮ ቅዱስ እግዚአብሔር፣ ከወንድሞቻችን እንደለየኸን እናምናለን፤ እናም በአባቶቻቸው ሞኝነት የተሰጧቸውን የወንድሞቻችንን ወግ አናምንም፣ ነገር ግን አንተ እኛ [ሀ]ቅዱሳን ልጆችህ እንድንሆን [ለ]እንደመረጥከን እናምናለን፣ እናም ደግሞ ክርስቶስ እንደሌለ እንድናውቅ አድርገኸናል።

፲፯ ነገር ግን አንተ ትናንትም፣ ዛሬም ለዘለዓለም አንድ ነህ፤ እናም በዙሪያችን ያሉ ሁሉ በቁጣህ ወደሲኦል እንዲጣሉ በተመረጡ ጊዜ፣ እኛ እንድንድን [ሀ]መርጠኸናል፤ ስለዚህም ስለቅድስናችን አቤቱ እግዚአብሔር እናመሰግንሀለን፣ እናም ደግሞ በክርስቶስ በማመን በሚያስተሳስራቸው፣ ልባቸውን ከአንተ ከሚያርቀው በወንድሞቻችን ከንቱ ወግ እንዳንመራ ስለመረጥኸን እናመሰግንሀለን።

፭ *ሀ* ዕብ. ፬፡ ፲፪፤ ያዕቆ. ፪፡ ፰፤ አልማ ፴፯፡ ፳፯።
ለ ኢኖስ ፩፡ ፳፫፤ አልማ ፬፡ ፲፱። ቅ.መ.መ. መስበክ።

ሐ ጄረም ፩፡ ፲፩–፲፪፤ ት. እና ቃ. ፲፩፡ ፪።

፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. ሔለማን፣ የአልማ ልጅ።
ለ አልማ ፴፡ ፶፬።

፰ *ሀ* አልማ ፳፭፡ ፴፡ ፴፰።

፱ *ሀ* ቅ.መ.መ. ክህደት።

፲፡ *ሀ* ማቴ. ፮፡ ፩–፯።

፲፯ *ሀ* ኢሳ. ፳፭፡ ፲፡ ፭።
ለ አልማ ፴፳፡ ፲፫–፲፡ ፡ ፲፡ *ሀ* ቅ.መ.መ. ከንቱ፣ ከንቱነት።

፲፰ እናም አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ፣ እኛ የተመረጥንና ቅዱስ ሰዎች በመሆናችን በድጋሚ እናመሰግንሀለን። አሜን።

፲፱ እንግዲህ እንዲህ ሆነ አልማና ወንድሞቹ፣ እናም ልጆቹ ይህንን ፀሎት ከሰሙ በኋላ ያለመጠን ተገረሙ።

፳ እነሆም፣ ሁሉም ሰው ሄዶ ይህንኑ ፀሎት አቀረበ።

፳፩ እንግዲህ የስፍራው ስም ራሜዩምጵቶም ተብሎ ይጠራ ነበር፤ እርሱም ትርጓሜው ቅዱስ መቆሚያ ማለት ነው።

፳፪ እንግዲህ ከዚህ መቆሚያ እያንዳንዱ ሰው ይኸንኑ ፀሎት ያቀርባል፤ አምላካቸውን በእርሱ ስለተመረጡ፣ እናም እርሱም በወንድሞቻቸው ወግ እንዳይመሩ ስላደረገ፣ እናም ልባቸው ምንም ስለማያውቁት ስለሚመጡት ነገሮችም ስላልተወሰደ አምላካቸውን አመሰገኑት።

፳፫ አሁን፣ ህዝቡ በዚህ ሁኔታ ምስጋናውን ካቀረበ በኋላ ወደ ቤቱ ተመለሰ፤ በቅዱሱ መቆሚያ ተሰብስበው በድጋሚ በዚህ ሁኔታ ምስጋናን እስከሚያቀርቡ ድረስ ስለ አምላካቸውም በድጋሚ ″አልተናገሩም።

፳፬ እንግዲህ አልማ ይህንን በተመለከተ ጊዜ ልቡ ″አዝኖ ነበር፤ እርሱ ኃጢአተኛና ብልሹ የሆኑትን ሰዎች መሆናቸውን ተመልክቷልና፤ አዎን ልባቸውንም በወርቅ፣ በብር፣ እናም በሚያምሩ ነገሮች ላይ ማድረጋቸውን ተመለከተ።

፳፭ አዎን እናም ደግሞ ልባቸው በኩራታቸው በፉከራ ″ሲነሳሳ ተመለከተ።

፳፮ እናም ድምፁን ወደሰማይ ከፍ አደረገና፣ እንዲህ በማለት ″ጮኸ፥ አቤቱ ጌታ ሆይ አገልጋዮችህ በሰው ልጆች መካከል እንደዚህ ዓይነቱን ታላቅ ኃጢያት ሲሰሩ ለመመልከት እስከመቼ ከዚህ በታች በስጋ እንዲኖሩ ትፈቅዳለህ?

፳፯ እነሆ፣ አምላክ ሆይ፣ እነርሱ ወደአንተ ″ይጮኻሉ፣ እናም ይሁን እንጂ ልባቸው በኩራታቸው ተሞልቷል። እነሆ፣ አምላክ ሆይ፣ በዓለም ከንቱ ነገሮች እስከ ^ማበጥ ድረስ ሲኩራሩ በአንደበታቸው ግን ወደአንተ ይጮሃሉ።

፳፰ አምላኬ ሆይ፣ ውድ ልብሶቻቸውም፣ ቀለበቶቻቸውም፣ ″አምባሮቻቸውንም፣ የወርቅ ጌጣጌጦቻቸውንም፣ እናም የሚያጌጡባቸው የተከበሩ ነገሮቻቸው ሁሉ ተመልከት፤ እናም እነሆ ልባቸው በእነዚህ ላይ ነበር፣ ግን ወደ አንተ ይጮሀሉም እንዲህም ይላሉ—ሌሎች በሚጠፉበት ጊዜ እኛ በአንተ የተመረጥን ስለሆነ አምላክ ሆይ እናመሰግንሀለን።

፳፱ አዎን፣ እናም አንተ ክርስቶስ አለመኖሩን እንዳሳወቅሃቸውም ይናገራሉ።

፴ ጌታ አምላክ ሆይ፣ እንደዚህ ዓይነት ክፋትን እና ታማኝ አለመሆንን በዚህ ህዝብ መካከል ለምን ያህል ጊዜ ትፈቅዳለህ? ጌታ ሆይ፣ በደካማነቴ እታገስ ዘንድ ብርታትን ትሰጠኛለህ። ምክንያቱም እኔ ደካማ ነኝና፣ እናም በእነዚህ ሰዎች መካከል እንደዚህ ዓይነት ክፋት ነፍሴን ያስጨንቃታል።

፴፩ አምላክ ሆይ፣ ልቤ እጅግ አዝኗል፤ ″በክርስቶስ ነፍሴን ታፅናናለህን። ይህንንም በእኔ ላይ በህዝቡ ክፋት የሚመጣውን ስቃይ በትዕግስት እታገሰው ዘንድ ጌታ ሆይ ብርታትን ትሰጠኛለህ።

፴፪ ጌታ ሆይ፣ ነፍሴን ታፅናናለህ፣ እናም ለእኔና፣ ደግሞ ከእኔ ጋር ለሚያገለግሉት ጓደኞቼ—አዎን፣ አሞንና፣ አሮንንም፣ ኦምነርንም፣ ደግሞ አሙሌቅንም፣ ዚኤዝሮምንም፣ እናም ደግሞ ″ሁለት ወንድ ልጆቼንም—መቃናትን ስጠን፤ አዎን፣ ጌታ ሆይ፣ እነኝህን ሁሉ ታፅናናለህ። አዎን በክርስቶስ ነፍሳቸውን ታፅናናለህ።

፳፫ ″ ያዕ. ፩፡ ፳፩–፳፭።
፳፬ ″ ዘፍጥ. ፮፡ ፭–፯።
፳፭ ″ ያዕቆ. ፪፡ ፲፫፣ አልማ ፩፡ ፴፪።
፳፮ ″ ሙሴ ፯፡ ፶፩–፶፭።
፳፯ ″ ኢሳ. ፳፱፡ ፲፫።
ለ ቅ.መ.መ. ኩራት።
፳፰ ″ ኢሳ. ፫፡ ፲፯–፳፬።
፴ ″ ዮሐ. ፲፯፡ ፴፫።
፴፩ ″ አልማ ፴፩፡ ፯።

፴፫ በህዝቡ ክፋትም የተነሳ በእነርሱ ላይ የሚመጣውን ስቃይ ይሸከሙ ዘንድ ብር ታትን እንዲያገኙ ትሰጣቸዋለህ።

፴፬ ጌታ ሆይ፣ እኛም በድጋሚ እነርሱን ወደ ክርስቶስ በማምጣት ድልን እናገኝ ዘንድ ለእኛ ᵐትፈቅድልናለህ።

፴፭ እነሆ፣ ጌታ ሆይ፣ የእነርሱ ᵐነፍስ ውድ ነው፣ እናም ብዙዎቹ ወንድሞቻችን ናቸው፤ ስለዚህ ጌታ ሆይ፣ እነዚህን ወን ድሞቻችንን በድጋሚ ወደአንተ እናመጣ ቸው ዘንድ ኃይልና ጥበብን ስጠን።

፴፮ እንግዲህ እንዲህ ሆነ አልማ እነዚ ህን ቃላት በተናገረ ጊዜ፣ ከእርሱ ጋር በነ በሩት ላይ ሁሉ ᵐእጁን ᵃአጨበጨበ። እናም እነሆ፣ እጁን በእነርሱ ላይ ባጨበጨበ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ።

፴፯ እናም ምን መመገብ እንዳለባቸውም ሆነ መጠጣት እንዳለባቸው እንዲሁም ምን ማድረግ እንዳለባቸው ᵐሳያስቡ አንዳቸው ከሌላኛው እራሳቸውን ለዩ።

፴፰ እናም ጌታ እንዳይራቡ ወይም እን ዳይጠሙ ሁሉን አቀረበላቸው፤ አዎን፣ እናም ደግሞ በክርስቶስ ፍቅር ከመዋጥ በስ ተቀር ምንም ᵐስቃይ እንዳያገኛቸው ብር ታትን ሰጣቸው። እንግዲህ ይህም በአልማ ፀሎት መሰረት የሆነ ነበር፤ እና ይህ ደግሞ እርሱ ᵃበእምነት በመፀለዩ ነበር።

ምዕራፍ ፴፪

አልማ ስቃያቸው ትሁት ያደረጋቸውን ድሆች አስተማረ—እምነት በዚያ በማይ ታየው እውነት በሆነው የሚደረግ ተስፋ ነው—አልማ መላዕክት ለወንዶች፣ ለሴ ቶች፣ እና ለልጆች እንደሚያገለግሉ መሰከረ—አልማ ቃሉን ከዘር ጋር አነፃ ፀረ—ይህም መተከልና እንክብካቤ ሊደ ረግለት ይገባዋል—ከእዚያም የዘለዓለም ህይወት የሆነው ፍሬ ወደሚሰበሰብበት ያድጋል። በ፳፭ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ እነርሱ ሄዱና፣ በሰ ዎቹ ምኩራብና፣ በቤታቸው በመግባት የእ ግዚአብሔርን ቃል መስበክ ጀመሩ፤ አዎን እናም ቃሉን በእነርሱ መንገድም እንኳን ሰበኩ።

፪ እናም እንዲህ ሆነ በመካከላቸው ብዙ ከሰሩ በኋላ፣ ᵐበደሃው ህዝብ መካከል መል ካም ውጤት ማግኘት ጀመሩ፤ ምክንያ ቱም፣ እነሆ፣ በልብሳቸው ቆሻሻነት የተ ነሳ ከምኩራቡ ተባርረው ነበርና—

፫ የረከሱ ናቸው ተብሎ ስለተቆጠሩ እግ ዚአብሔርን ለማምለክ ወደ ምኩራብ ለመ ግባት አልተፈቀደላቸውም ነበር፤ ስለዚህ እነርሱ ᵐድሆች ነበሩ፤ አዎን፣ በወንድሞ ቻቸው እንደ አተላ ተቆጥረው ነበር፤ ስለ ዚህ በዓለም ነገሮች ድሆች ነበሩ፤ እናም ደግሞ በልባቸውም ድሆች ነበሩ።

፬ አሁን፣ አልማ በኦኒዳ ኮራብታ ላይ ለህ ዝቡ ሲያስተምር፣ እና ሲናገር ስለእነርሱም እኛ የተናገርነው፣ በዓለም ነገሮች ድሆች የሆኑት፣ እና ᵐበልባቸው ድሃ የሆኑ ብዙ ህዝብ ወደ እርሱ መጡ።

፭ እናም እነርሱ ወደአልማ መጡ፤ እናም ከመካከላቸው ዋና የሆነው እንዲህ አለው፥ እነሆ ᵐእነኚህ ወንድሞቼ ምን ያድርጉ፤ ምክንያቱም እነርሱ በድህነታቸው በሰዎች ሁሉ፣ አዎን በተለይ በካህናቶቻችን፣ ተጠ ልተዋል፤ ምክንያቱም በእራሳችን እጆች በእጅግ ጥረን ከሰራናቸው ከምኩራቦቻችን ᵃአስወጥተውናል፤ እጅግ ድሆች በመሆና ችንም እኛን አባረውናል፤ አምላካችንንም ለማምለክ ምንም ስፍራ የለንም፤ እናም እነሆ ᵃምን ማድረግ አለብን?

፴፩ ᵐ ፪ ኔፊ ፳፯፡ ፴፫።
፴፫ ᵐ ቅ.መ.መ. ነፍስ—የነፍሶች ዋጋ።
፴፬ ᵐ ቅ.መ.መ. እጅን መጫን።
ᵃ ፫ ኔፊ ፲፰፡ ፴፯–፴፱።
፴፯ ᵐ ማቴ. ፮፡ ፳፭–፴፩፤ ፫ ኔፊ ፲፫፡ ፴–፴፩፤ ፫ ኔፊ ፲፫፡ ፴፩።
፴፰ ᵐ ፪ ኔፊ ፱፡ ፲፰፤ ሞዛያ ፳፩፡ ፲፫–፲፭፤ አልማ ፴፫፡ ፳፫።
ᵃ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
፴፪ ᵐ ቅ.መ.መ. ደሀ።
፫ ᵐ አልማ ፴፩፡ ፵።
፬ ᵐ ቅ.መ.መ. ደሀ—በመንፈስ ደሀነት።
፭ ᵐ ምሳ. ፲፰፡ ፳፫።
ᵃ አልማ ፴፫፡ ፲።
ሐ የሐዋ. ፪፡ ፴፯–፴፰።

፮ እናም አሁን አልማ ይህንን በሰማ ጊዜ፣ አልማ ፊቱን በፍጥነት ወደ እርሱ አዞረ፣ እናም በታላቅ ደስታ ተመለከተ፤ ምክን ያቱም *ስቃያቸው በእውነት እራሳቸውን ^ዝቅ እንዳደረገና፣ እነርሱ ቃሉን ለመስ ማት ^በዝግጅት ላይ እንደነበሩ ተመለከተ።

፯ ስለዚህ ለሌሎቹ ሰዎች ምንም አልተ ናገረም ነበር፣ ነገር ግን ለሚመለከታቸው፣ በእውነት ለተፀፀቱት እጁን ዘረጋና፣ ጮኸ፣ እናም እንዲህ አላቸው፥

፰ እነሆ በልባችሁ *ትሁት እንደሆናችሁ እመለከታለሁ፤ እናም እንደዚያ ከሆናችሁ የተባረካችሁ ናችሁ።

፱ እነሆ ወንድማችሁ ምን ማድረግ አለ ብን? ይላል—ከምኩራባችን ስለተባረርን፣ አምላካችንን ማምለክ አንችልም።

፲ እነሆ እንዲህ እላችኋለሁ፣ በምኩራ ባችሁ ብቻ ካልሆነ *እግዚአብሔርን ለማ ምለክ አንችልም ብላችሁ ታስባላችሁን?

፲፩ እናም ከዚህ በተጨማሪ እጠይቃች ኋለሁ፣ በሳምንት አንድ ጊዜ ብቻ እግዚ አብሔርን ማምለክ እንዳለባችሁ ትገምታ ላችሁን?

፲፪ እንዲህ እላችኋለሁ፣ ትሁት ትሆኑ፣ እናም *ጥበብን ዘንድ ከምኩራባችሁ መባ ረራችሁ መልካም ነው፤ ምክንያቱም ጥበ ብን መማራችሁ አስፈላጊ ነው፤ በመባረ ራችሁ፣ በእጅግ ^ድሀነታችሁ በወንድሞ ቻችሁ ስለተጠላችሁ ምክንያት ነው ልባ ችሁን ትሁት የሆነው፤ ትሁትም የሆናች ሁትም ተገድዳችሁ ነው።

፲፫ እናም እንግዲህ፣ ትሁት እንድትሆኑ በመገደዳችሁ እናንተ የተባረካችሁ ናችሁ፤ አንዳንዴ ሰው ትሁት እንዲሆን ከተገደደ ንስሃን ይሻልና፤ እናም አሁን በእርግጥ ንስሃ የገባ ሁሉ ምህረትን ያገኛል፤ እናም ምህረ ትን ያገኘና፣ እስከመጨረሻው *የፀና እርሱ ይድናል።

፲፬ እናም አሁን፣ እኔ እንደተናገርኳችሁ፣ ትሁት እንድትሆኑ በመገደዳችሁ የተባረካ ችሁ ናችሁ፤ በቃሉም የተነሳ በእውነት ዝቅ ያሉ ከዚህ የበለጠ የተባረኩ ናቸው ብላችሁ አትገምቱምን?

፲፭ አዎን፣ በእውነት እራሱን ዝቅ ያደረ ገና፣ ለኃጢአቱ ንስሃ የገባ፣ እናም እስከመ ጨረሻው የፀና፣ እርሱ ይባረካል—አዎን፣ በከፋው ድህነታቸው ዝቅ እንዲሉ ከተገደ ዱት የበለጠ በብዙ ይባረካል።

፲፮ ስለዚህ እራሳቸውን ዝቅ እንዲያደ ርጉ ሳይገደዱ እራሳቸውን *ዝቅ ያደረጉት የተባረኩ ናቸው፤ ወይንም በሌላ አነጋገር፣ በእግዚአብሔር ቃል ያመነ፣ አዎን፣ ቃሉን እንዲያውቅ ሳይገደድ በልቡም ሳያመነታ የተጠመቀ፣ እርሱ የተባረከ ነው።

፲፯ አዎን፣ እንዲህ የሚሉ ብዙዎች አሉ፥ ከሰማይ *ምልክትን ካሳየኸን፣ እርግጠኛ ነቱን እናውቃለን፣ ከዚያም እናምናለን።

፲፰ እንግዲህ እንዲህ ብዬ እጠይቃለሁ፥ ይህ እምነት ነውን? እነሆ፣ እንዲህ እላች ኋለሁ፤ አይደለም፣ ሰው ነገርን የሚያውቅ ከሆነ *ለማመን ምንም መንስኤ የለውም፣ ያውቀዋልና።

፲፱ እናም እንግዲህ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ *እያወቀ የማያደርገው ከሚያም ነው፣ ወይም የማመን ምክንያት ያለው እና በመተላለፍ ከሚወድቀው እንዴት ይበልጥ የተረገመ ነው?

፳ እንግዲህ ይህን ነገር በተመለከተ መፍ ረድ አለባችሁ። እነሆ፣ እንዲህ እላችኋለሁ በአንድ በኩል የሆነው በሌላ በኩልም ይሆ ናል፤ እናም ለእያንዳንዱ ሰው እንደስራው ይሆንለታል።

፳፩ እናም አሁን እምነትን በተመለ ከተ እንደተናገርኩት፣ *እምነት ስለ ነገ ሮች ፍፁም የሆነ እውቀት አለ ማለት አይ ደለም፤ ስለዚህ እምነት ካላችሁ እውነት

፮ *ሀ* ቅ.መ.መ. ጭንቀት።
ለ ቅ.መ.መ. ትሁት፣ ትሕትና።
ሐ አልማ ፲፯፡ ፲፯–፲፯፤ ት. እና ቃ. ፲፩፡ ፲፡
፰ *ሀ* ማቴ. ፭፡ ፣–፮።
፲ *ሀ* ቅ.መ.መ. ማምለክ።
፲፪ *ሀ* መክ. ፬፡ ፣፣።
ለ ምሳ. ፲፯፡ ፡፡
፲፣ *ሀ* አልማ ፴፯፡ ፪።
፲፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. ትሁት፣ ትሕትና።
፲፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. ምልክት።
፲፡ *ሀ* ኤተር ፲፪፡ ፣፪፣ ፣፡፡
፲፱ *ሀ* ዮሐ. ፣፭፡ ፳፪–፳፬።
፳፩ *ሀ* ዮሐ. ፳፡ ፳፱፤ ዕብ. ፣፩።

ስለሆኑትና [ለ]ስለማይታዩት ነገሮች [ሐ]ተስፋ ይኖራችኋል።

፳፪ እናም አሁን፣ እነሆ፣ እንዲህ እላ ችኋለሁ፣ እግዚአብሔር በስሙ ለሚያ ምኑት ሁሉ መሃሪ መሆኑን እንድታስታ ውሱም እፈልጋለሁ፤ ስለዚህ በመጀመሪያ ደረጃ በእርሱ እንድታምኑ፤ አዎን በቃሉም እንኳን እንድታምኑ ይፈልጋል።

፳፫ እናም አሁን፣ ቃሉን በመላዕክት አማካኝነት ለወንዶች፣ አዎን፣ [መ]ለወንዶች ብቻ ሳይሆን ለሴቶችም እንዲሁ ይሰጣል። እንግዲህ ይህ ብቻም አይደለም፣ ጥበበኞ ችን እና የተማሩትን የሚያምታቱ ቃላት ህፃናት [ሀ]ልጆች ብዙ ጊዜም ይሰጣቸዋል።

፳፬ እናም አሁን፣ የተወደዳችሁ ወንድ ሞች፣ እናንተ የተሰቃያችሁና የተጣላችሁ በመሆናችሁ ምክንያት ምን ማድረግ እን ዳለባችሁ ከእኔ ለማወቅ በመፈለጋችሁ—አሁን እናንተን በዚያ እውነት በሆነው ብቻ ልፈርድባቸሁ እንደሆነ እንድትገምቱ አል ፈልግም—

፳፭ ሁላችሁም ራሳችሁን ዝቅ እንድታደ ርጉ ተገድዳችኋል ማለቴም አይደለምና፤ ጉዳያቸው ምንም ቢሆንም ከእናንተ መካ ከል እራሳቸውን ዝቅ የሚያደርጉ ጥቂቶች እንዳሉ በእርግጥ አምናለሁ።

፳፮ እንግዲህ፣ እምነትን በተመለከተ እንደተናገርኩት—ፍፁም እውቀት አይ ደለም—የእኔም ቃል እንዲህ ነው። እምነ ትም ፍፁም ዕውቀት እንዳልሆነ፣ በቅድ ሚያ የእርሱን እርግጠኛነት በፍፁም ልታ ውቁ አይቻላችሁም።

፳፯ ነገር ግን እነሆ፣ አዕምሮአችሁን ካነ ቃችሁት፣ እናም ካነሳሳችሁት፣ በቃሌም እስከምትለማመዱ እንኳን፣ እናም ቅንጣት ያህል እምነትን ከተለማመዳችሁ፣ አዎን ከማመን በላይ የበለጠ [መ]ለመፈለግ ባትች ሉም፣ ለቃላቴ በውስጣችሁ ትንሽ ቦታ ለመስጠት እስከምትችሉ ድረስ ይህ ፍላ ጎት በእናንተ እንዲሰራ አድርጉ።

፳፰ እንግዲህ፣ ቃሉን [ሠ]ከዘር ጋር እና ነፃራለን። እንግዲህ፣ [ረ]ዘሩ [ሐ]በልባችሁ ውስጥ እንዲተከል ሥፍራን ከሰጣችሁት፣ እነሆ፣ እውነተኛ ዘር ከሆነ ወይም መልካም ዘር ከሆነ፣ [ሠ]ባለማመናችሁ የጌታን መንፈስ በመቃወም የማትጥሉት ከሆነ፣ እነሆ፣ እር ሱም በደረታችሁ ውስጥ ማደግ ይጀምራል፤ እናም ይህ ዕድገት በልባችሁ ውስጥ ሲሰማ ችሁ፣ በውስጣችሁ እንዲህ ማለት ትጀምራ ላችሁ—ይህ መልካም ዘር መሆን አለበት፣ ወይንም ቃሉ መልካም ነው፣ ምክንያቱም በነፍሴ ውስጥ ማደግ ጀመሯልና፤ አዎን [ሠ]ግንዛቤዬን ያበራልኝ ጀምሯል፤ አዎን፣ ለእኔም አስደሳች መሆን ጀምሯል።

፳፱ እናም እነሆ፣ ይህ እምነታችሁን አያሳድግላችሁምን? እኔ እንዲህ እላች ኋለሁ፣ አዎን፣ ይሁን እንጂ እምነታችሁ ወደፍፁም እውቀት ከፍ ባይልም እንኳን ይህ እምነታችሁን አያሳድገውምን?

፴ ነገር ግን እነሆ፣ ዘሩ በፋፋና በበቀለ፣ እናም ማደግ በጀመረ ጊዜ፣ ከዚያም ዘሩ መልካም ነው ማለት አለባችሁ፤ ምክን ያቱም እርሱ ይፋፋልም፣ ይበቅላልም፣ ማደግ ይጀምራልም። እናም አሁን እነሆ፣ ይህ እምነታችሁን አያጠነክርምን? አዎን፣ እምነታችሁን ያጠነክራል፤ ምክንያቱም ይህ መልካም ዘር እንደሆነ አውቃለሁ ትላ ላችሁና፤ ምክንያቱም እነሆ በቅሏል እናም ማደግ ጀምሯል።

፴፩ እናም አሁን፣ እነሆ፣ ይህ መልካም ዘር ለመሆኑ እርግጠኞች ናችሁን? እኔ እን ዲህ እላችኋለሁ፤ አዎን፣ ማንኛውም ዘር እራሱን [መ]መሰል ዘር ይሰጣል።

፴፪ ስለዚህ፣ ዘሩ የሚያድግ ከሆነ መል ካም ነው፤ ነገር ግን የማያድግ ከሆነ፣ እነሆ መልካም አይደለም ስለዚህ ይጣላል።

፳፩ *ለ* ኤተር ፲፪፡፮።
ሐ ቅ.መ.መ. ተስፋ።
፳፫ *ሀ* ኢዩ. ፪፡፳፰–፳፱።
ለ ማቴ. ፲፩፡፳፭፤
ሉቃ. ፲፡፳፩፤
ፊ ኔፊ ፳፯፡፲፬–፲፮፤
ት.እና ቃ. ፻፳፰፡፲፰።
፳፯ *ሀ* ማር. ፲፩፡፳፬።
፳፰ *ሀ* አልማ ፴፫፡፩።
ለ ሉቃ. ፰፡፲፩።
ሐ ቅ.መ.መ. ልብ።
መ ማቴ. ፲፯፡፳።
ሠ ቅ.መ.መ. ማስተዋል።
፴፩ *ሀ* ዘፍጥ. ፩፡፲፩–፲፪።

፴፫ እናም አሁን እነሆ ልምምዱን በመሞ ከራችሁና፣ ዘሩን በመትከላችሁ፣ እርሱም በመፋፋቱና፣ በመብቀሉ፣ እናም ማደግ በመጀመሩ ዘሩ መልካም መሆኑን ማወቅ ይገባችኋል።

፴፬ እናም እንግዲህ፣ እነሆ፣ [a]እውቀታ ችሁ ፍፁም ነውን? አዎን፣ እውቀታችሁ በእዚያ ነገር ፍፁም ነው፣ [b]እምነታችሁም ዘገምተኛ ነው፤ እናም ይህንን በማወቃችሁ፣ ቃልም ነፍሶቻችሁን እንደሚያፋፋ ታውቃ ላችሁ፣ ደግሞም መብቀሉን ስላወቃችሁ፣ ግንዛቤአችሁ ብርሃን ማግኘት ይጀምራል፣ እናም [c]አዕምሮአችሁ መስፋፋት ጀምሯል።

፴፭ አቤቱ ይህ እውነት አይደለምን? እኔ እንዲህ እላችኋለሁ፤ አዎን፣ ምክንያቱም ይህ [d]ብርሃን ነው፣ እናም ብርሃን የሆነው ማንኛውም መልካም ነው፣ ምክንያቱም እርሱ የሚለይ ነውና፣ ስለሆነም መልካም መሆኑን ማወቅ ይገባችኋል፤ እናም አሁን እነሆ፣ ይህንን ብርሃን ከሞከራችሁት በኋላ እውቀታችሁ ፍፁም ይሆናልን?

፴፮ እነሆ አይደለም እላችኋለሁ፣ ወይም እምነታችሁን መተው የለባችሁም፣ ምክን ያቱም ዘሩ መልካም መሆኑን ለማወቅ ልም ምዱን ትሞክሩ ዘንድ፣ ዘሩን ለመትከል ብቻ እምነታችሁን ተለማምዳችኋልና።

፴፯ እናም እነሆ፣ ዛፍ ማደግ ሲጀምር፣ እንዲህ ትላላችሁ፥ ስርን እንዲያገኝ፣ እር ሱም እንዲያድግ፣ እናም ፍሬን እንዲያስ ገኝልን፣ በታላቅ ጥንቃቄ እንንከባከበው። እናም አሁን እነሆ፣ በተገቢው ጥንቃቄ ከተ ንከባከባችሁት ስር ያገኛልም፣ ያድጋልም፣ እናም ፍሬን ያስገኛል።

፴፰ ነገር ግን ዛፉን [e]ከተዋችሁትና፣ ለእ ንክብካቤው ማሰብ ካቆማችሁ፤ እነሆ ስር አያገኝም፤ እናም የፀሐይ ሙቀት መጥቶ ባቃጠለው ጊዜ፣ ስር ስለሌለው ይደርቃል፤ እናም ትቆርጡትና ትጥሉታላችሁ።

፴፱ እንግዲህ፣ ይህም የሆነው ዘሩ መል ካም ስላልነበረ አይደለም፤ ወይም ፍሬውም ቢሆን ተፈላጊ ባለመሆኑ አልነበረም፣ ነገር ግን [f]መሬታችሁ መካን በመሆኑ፣ እናም ዛፉን አትንከባከቡትም፤ ስለዚህ የዚህን ፍሬ አታገኙም።

፴ እናም ለእዚያ ፍሬ በእምነት ዓይን በመጠበቅ እንደዚህ ቃሉን የማትንከባካ ቡት ከሆነ፣ [g]ከህይወት ዛፍ ፍሬ በጭራሽ መቅጠፍ አትችሉም።

፴፩ ነገር ግን ቃሉን የምትንከባከቡ ከሆነ፣ አዎን በእምነታችሁ በታላቅ ትጋት፣ [h]ትዕ ግስት፣ እና ለዚያ ፍሬ በጉጉት በመጠበቅ የምትንከባከቡት ከሆነ፣ ይህም ስር ያወ ጣል፤ እናም እነሆ ይህም ወደ ዘለዓለማዊው ህይወት [i]የሚያድግ ዛፍ ይሆናል።

፴፪ እናም ስር እንዲያወጣ ዘንድ ቃሉን ለመንከባከብ [j]ትጉ በመሆናችሁና፣ በታ ማኝነታችሁ እንዲሁም በትዕግስተኛነታ ችሁ፣ እነሆ፣ የተከበረውን፣ ከጣፋጮች ሁሉ ጣፋጭ የሆነውንና ከነጡት ሁሉ በላይ ነጭ፣ አዎን ከንፁህ ሁሉ በላይ ንፁህ የሆ ነውን [k]ፍሬ ከጊዜ በኋላ ትቀጥፋላችሁ፤ እናም እርሃባችሁ እስከሚጠፋና፣ ጥማታ ችሁ እስኪቆረጥ ድረስ እንኳን ቢሆን ይህ ንን ፍሬ ትመገባላችሁ።

፴፫ ከዚያም ወንድሞቼ፣ ዛፉ ፍሬ እን ዲያስገኝላችሁ በመጠበቃችሁ ለእምነታ ችሁ፣ ለትጋታችሁና፣ ለፅናታችሁ፣ እናም ለታጋሽነታችሁ ደመወዝን ታገኛላችሁ።

ምዕራፍ ፴፫

ዜኖስ ሰዎች በሁሉም ስፍራ መፀለይ፣ እና ማምለክ እንዳለባቸው፣ እናም ፍርድም በወልድ አማካኝነት እንደሚለውጥ አስ ተማረ—ዜኖቅ በወልድ አማካኝነት ምህ ረት እንደሚሰጥ አስተማረ—ሙሴ በም

---

[a] ሀ ቅ.መ.መ. እውቀት።
ለ ኤተር ፫ ፡ ፲፱።
ሐ ቅ.መ.መ. አዕምሮ።
[b] ሀ ዮሐ. ፫ ፡ ፲፰–፳፩።
ቅ.መ.መ. ብርሀን፣ የክርስቶስ ብርሀን።
[c] ሀ ቅ.መ.መ. ክህደት።
[d] ሀ ማቴ. ፲፫ ፡ ፭።
[e] ሀ ዘፍጥ. ፪ ፡ ፱፤
፩ ኔፊ ፲፭ ፡ ፴፯።
[f] ሀ ቅ.መ.መ. ትዕግስት።
ለ አልማ ፴፫ ፡ ፳፫፣
ት. እና ቃ. ፳፫ ፡ ፳፫።
[g] ሀ ቅ.መ.መ. ትጋት።
ለ ፩ ኔፊ ፲ ፡ ፲–፲፪።

ድረበዳው የእግዚአብሔርን ልጅ ምሣሌ የሆነውን አንስቷል። በ፫፴ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም አልማ እነዚህን ቃላት ከተናገረ በኋላ፣ እርሱ የተናገረውንም ፍሬ ያገኙ ዘንድ [ሀ]በአንድ አምላክ ማመን እንዳለባቸው፣ ወይንም [ለ]ዘሩን ወይም በልባቸው መትከል ይገባቸዋል ብሎ እርሱ ስለተናገረው ቃል እንዴት እንደሚተክሉ፣ ወይም እንግዲህ በምን ዓይነት ሁኔታ እምነትን መለማመድ እንዳለባቸው ለማወቅ በመፈለግ ላኩበት።

፪ እናም አልማ እንዲህ አላቸው፥ እነሆ፣ ከምኩራባችሁ በመባረራችሁ አምላካችሁን [ሀ]ማምለክ እንደማትችሉ ተናግራችኋል። ነገር ግን እነሆ፣ እንዲህ እላችኋለሁ፤ አምላክን ማምለክ አንችልም ብላችሁ ከገመታችሁ እጅግ ተሳስታችኋል፤ እናም [ለ]ቅዱሳት መፃሕፍትን መመርመር አለባችሁ፤ ይህንን አስተምረውናል ብላችሁ ከገመታችሁ አልተረዳችኋቸውም።

፫ የጥንቱ ነቢይ [ሀ]ዜኖስ፣ ፀሎትን እና [ለ]አምልኮትን በተመለከተ የተናገረውን ማንበባችሁን ታስታውሳላችሁን?

፬ እርሱም እንዲህ ብሏልና፥ እግዚአብሔር ሆይ፣ ፀሎቴን በምድረበዳው በነበርኩበት ጊዜም እንኳን ስለሰማኸኝ አንተ መሃሪ ነህ፤ አዎን፣ [ሀ]ጠላቶቼ ለሆኑትም ለእነዚያ በፀለይኩኝ ጊዜ መሃሪ ነበርክ፣ እናም እነርሱም ለእኔ ደግ እንዲሆኑልኝ አድርገሃል።

፭ አዎን፣ እግዚአብሔር ሆይ፣ እናም [ሀ]በስፍራዬ ሆኜ ወደአንተ ስጮህ ምህረትን ሰጥተኸኛል፣ በፀሎቴ ወዳንተ ስጮህ እነሆ ሰምተኸኛል።

፮ እናም በድጋሚ አቤቱ እግዚአብሔር ወደቤቴም በተመለስኩኝ ጊዜ ፀሎቴን ሰምተሃል።

፯ እናም፣ ጌታ ሆይ፣ ወደ [ሀ]እልፍኜም በሄድኩኝ ጊዜና ወደ አንተ በፀለይኩ ጊዜ ሰምተኸኛል።

፰ አዎን ልጆችህ በሰዎች ሳይሆን በአንተ እንዲሰሙ ወደ አንተ ሲጮሁ መሃሪ ነህ፣ እናም አንተ ትሰማቸዋለህ።

፱ አዎን፣ እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ ለእኔ መሃሪ ሆነሀል፣ እናም በጉባዔህም መካከል ጩኸቴን ሰማህ።

፲ አዎን፣ እናም [ሀ]በተጣልኩና በጠላቶቼ በተጠላሁ ጊዜ ደግሞ ሰምተኸኛል፤ አዎን፣ ጩኸቴን ሰምተሃልና፣ በጠላቶቼም ተቆጥተሃል፣ እናም በፈጣኑ ጥፋትህም በቁጣህ ጎብኝተሃቸዋል።

፲፩ እናም በሥቃዬና በቅንነቴ ምክን ያት ሰምተኸኛል፤ እናም በልጅህ አማካኝነት ለእኔ መሃሪ ሆነሃል፤ ስለዚህ በስቃዬ ሁሉ ወደአንተ እጮሀለሁ፣ ደስታዬ በአንተ ነውና፤ በልጅህ አማካኝነት ፍርድህን ከእኔ አርቀሃልና።

፲፪ እናም አሁን አልማ እንዲህ አላቸው፥ በጥንት ነቢያት የተፃፉትን እነዚያን [ሀ]ቅዱሳት መጻሕፍት ታምናላችሁን?

፲፫ እነሆ፣ የምታምኑ ከሆነ፣ [ሀ]ዜኖስ የተናገረውን ማመን አለባችሁ፤ እነሆ እርሱ እንዲህ ብሏልና፥ በልጅህ አማካኝነት ቅጣትህን አርቀሀል።

፲፬ እናም እነሆ፣ ወንድሞቼ፣ ቅዱሳን መጽሐፍትን አንብባችሁ እንደሆን እጠይቃችኋለሁ? ካነበባችሁ የእግዚአብሔርን ልጅ እንዴት ላታምኑ ትችላላችሁ?

፲፭ ስለእነዚህ ነገሮች የተናገረው ዜኖስ ብቻ ነው ተብሎ [ሀ]አልተጻፈም፣ ነገር ግን [ለ]ዜኖቅ ደግሞ ስለእነዚህ ነገሮች ተናግሯል—

፴፫ ፩ ሀ ፪ ኔፊ ፴፩፡፳፩፤ ሞዛያ ፲፭፡፪–፬። ለ አልማ ፴፪፡፳፫–፴፫። ፪ ሀ አልማ ፴፪፡፭። ለ አልማ ፴፯፡፣ ፲–፲፡ ፣ ሀ ቅ.መ.መ. ቅዱሳት መጻህፍት—የጠፉ ቅዱሣት መጻህፍት፤ ዜኖስ። ለ ቅ.መ.መ. ማምለክ። ፩ ሀ ማቴ. ፭፡፴፩። ፭ ሀ አልማ ፴፩፡፳–፳፭። ፯ ሀ ማቴ. ፮፡፭–፮፤ አልማ ፴፩፡፳፯። ፣ ሀ አልማ ፴፪፡፭። ፣ ፪ ሀ ቅ.መ.መ. ቅዱሳት መጻህፍት። ፣ ፲ ሀ አልማ ፴፩፡፭። ፣ ፲፩ ሀ ያዕቆ. ፩፡፩። ለ ፩ ኔፊ ፲፱፡፲፤ አልማ ፴፩፡፯።

፲፯ እነሆም እርሱ እንዲህ ብሏል፡ ጌታ ሆይ፣ ይህ ህዝብ በልጅህ አማካኝነት የሰ ጠኸውን ምህረት ስለማይረዳ አንተ ተቆ ጥተሀል።

፲፰ እናም አሁን፣ ወንድሞቼ፣ ከጥንት ነቢያት ሁለተኛው ስለእግዚአብሔር ልጅ መስክሯል፣ እናም ህዝቡ ቃሉን ስላላመኑ በድንጋይ *ወግረው ገደሉት።

፲፱ ነገር ግን እነሆ፣ ይህ ብቻም አይደ ለም፤ ስለእግዚአብሔር ልጅ የተናገሩት እነዚህ ብቻ አይደሉም።

፲፱ እነሆ *ሙሴም ስለእርሱ ተናግሮ ነበር፤ አዎን፣ እናም እነሆ፣ ይህን ቀና ብሎ የተመለከተ እንዲኖር ዘንድ እንደ ^ምሳሌ የሆነው በምድረበዳው ^ተሰቅሎ ነበር። እናም ብዙዎች ተመለከቱና፣ በህ ይወት ኖሩ።

፳ ነገር ግን የነገሮቹን ትርጉም ጥቂቶች ብቻ ተረዱ፣ እናም ይህም የሆነው በልባ ቸው ጠጣርነት የተነሳ ነው። ነገር ግን ብዙ ልበ ጠጣሮች ስለነበሩ አልተመለከቱም፣ ስለዚህም ጠፉ። ያንንም ያልተመለከቱበት ምክንያት እነርሱን *እንደሚፈውስ ባለማ መናቸው ነበር።

፳፩ ወንድሞቼ ሆይ፣ ትፈወሱ ዘንድ በቀ ላሉ በዓይናችሁ በመመልከት ለመፈወስ የምትችሉ ከሆነ፣ በፍጥነት አትመለከቱ ምን፣ ወይንስ ትጠፉ ዘንድ ዐይኖቻችሁን በዚያ ላይ ባለማመንስ ልባችሁን ማጠጠር፣ እናም ሰነፍ መሆን ይሻላችኋልን?

፳፪ እንዲህ ከሆነ፣ ዋይታ በላያችሁ ይመ ጣባችኋል፤ ነገር ግን ይህም ካልሆነ፣ በዐ ይናችሁ ወደዚህና ወደዚያ ተመልከቱ፣ እናም የእግዚአብሔር ልጅ ህዝቡን ሊያ ድን እንደሚመጣና፣ ለህዝቡ *ኃጢያት ክፍያ እንደሚሰቃይና እንደሚሞት፣ እናም ሰዎች ^እንደስራቸው በመጨረሻውና በፍ ርዱ ቀን እንዲፈረድባቸው በፊቱ ይቆሙ ዘንድ ^ትንሳኤን ያመጣ ዘንድ በድጋሚ ከሙታን ^እንደሚነሳ *ማመን ጀምሩ።

፳፫ እናም አሁን፣ ወንድሞቼ፣ ይህን ቃል በልባችሁ *እንድትተክሉ እፈልጋለሁና፣ ማደግ በጀመረ ጊዜ በእምነታችሁ ተንከ ባከቡት። እናም እነሆ፣ እርሱም ዛፍ ይሆ ናል፣ እስከዘለዓለማዊው ህይወትም በእና ንተ ^ያብባል። በልጁም ደስታ አማካኝነት ^ሸክማችሁን እንዲቀልልላችሁ እግዚአ ብሔር ይፍቀድላችሁ። እናም ይህን ሁሉ እንኳን ከፈቀዳችሁ ማድረግን ትችላላ ችሁ። አሜን።

ምዕራፍ ፴፩

አሙሌቅ ቃሉ ለቤዛነታቸው በክርስቶስ ውስጥ መሆኑን መሰከረ—የኃጢያት ክፍ ያው ካልተደረገ፣ የሰው ዘር ሁሉ መጥ ፋት ነበረበት—የሙሴ ህጎች በሙሉ ወደ እግዚአብሔር ልጅ መስዋዕትነት ይጠ ቁማሉ—ዘለዓለማዊው የደህንነት ዕቅድ የተመሰረተው በእምነት እና በንስሃ ላይ ነው—ለጊዜያዊውና ለመንፈሳዊው በረ ከት ፀልዩ—ይህ ህይወት ሰዎች እግዚአ ብሔርን ለመገናኘት የሚዘጋጁበት ወቅት ነው—በእግዚአብሔር ፊት በፍርሀት የ ራሳችሁን ደህንነት አከናውኑ። በ፫፴ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም አሁን እንዲህ ሆነ አልማ እነ ዚህን ቃላት ከተናገራቸው በኋላ በመሬት ላይ ተቀምጦ ነበር፣ እናም *አሙሌቅ ተነ ሳና፣ እንዲህ በማለት እነርሱን ማስተማር ጀመረ፥

፪ ወንድሞቼ እንደማስበው የእግዚአብ

፲፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. ሰማዕት፣ ሰማዕትነት።
፲፱ *ለ* ዘዳግ. ፲፰ ፡ ፲፣ ፲፰፣ አልማ ፴፩ ፡ ፯።
ለ ዘኁል. ፳፩ ፡ ፱፣ ፪ ኔፊ ፳፭ ፡ ፳፣ ሞዛያ ፫ ፡ ፲፭።
ሐ ዮሐ. ፫ ፡ ፲፬፣ ሔለ. ፰ ፡ ፲፬–፲፭።
፳ *ሀ* ፩ ኔፊ ፲፯ ፡ ፴–፴፩።
፳፪ *ሀ* አልማ ፳፪ ፡ ፲፪፣ ፴፩ ፡ ፰–፱።
ለ ቅ.መ.መ. ስራዎች።
ሐ አልማ ፲፩ ፡ ፴፬።
መ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
ሠ አልማ ፴፪ ፡ ፳፯–፳፰።
፳፫ *ሀ* አልማ ፴፫ ፡ ፩፣ ፴፩ ፡ ፱።
ለ አልማ ፴፪ ፡ ፴፩፣ ት.እና ቃ. ፰፫ ፡ ፳፫።
ሐ አልማ ፴፩ ፡ ፴፰።
፴፱ ፩ *ሀ* አልማ ፰ ፡ ፳፩።

ሔር ልጅ ስለመሆኑ ያስተማርናችሁን የክ
ርስቶስን መምጣት በተመለከተ የተነገሩትን
ችላ ማለት የማይቻል ነው፤ አዎን፣ ከእኛ
ከመለየታችሁ በፊት ᵐእነዚህን ነገሮች በይ
በልጥ እንደተማራችሁት አውቃለሁ።

፲ እናም በስቃያችሁ የተነሳ ምን ማድ
ረግ እንዳለባችሁ እንዲያሳውቃችሁ የተ
ወደደውን ወንድሜን ለመጠየቅ በመፈለጋ
ችሁና፣ እርሱ የ ራሳችሁን አዕምሮ እንድ
ታዘጋጁ በመጠኑ ተናግሯል፤ አዎን እናም
እምነትና ትዕግስት እንዲኖራችሁ መክሯ
ችኋል—

፲፩ አዎን፣ የመልካምነቱን ልምምድ እን
ድትሞክሩት ዘንድ፣ ታላቅ እምነት ኖሯ
ችሁ ቃሉን በልባችሁ ᵐእንድትተክሉትም
መክሯችኋል።

፲፪ እናም ቃሉ በእግዚአብሔር ልጅ ውስጥ
መኖሩን፣ ወይም ክርስቶስ እንደሌለ ያላ
ችሁን ታላቅ ጥያቄ በአዕምሮአችሁ ውስጥ
እንደሆነ ተመልክተናል።

፲፫ እናም በብዙ ማስረጃዎች ᵐቃሉ ደህ
ንነት በክርስቶስ ውስጥ መሆኑን ወንድሜ
እንዳረጋገጠላችሁ ደግሞም ተመልክታ
ችኋል።

፲፬ ወንድሜም ቤዛነት በእግዚአብሔር
ልጅ አማካኝነት እንደሚመጣ የዜኖስን
ቃል፣ እናም ደግሞ የዜኖቅን ቃል፣ በመ
ጥቀስ ተናገረ፤ እናም ደግሞ እነዚህ ነገሮች
እውነት መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሙሴን
ቃላት ጠቀሰ።

፲፭ እናም አሁን፣ እነሆ፣ እኔ ራሴ እነዚህ
ነገሮች እውነት መሆናቸውን ᵐእመሰክራ
ለሁ። እነሆ፣ እንዲህም እላችኋለሁ፥ ክር
ስቶስ የህዝቡን መተላለፍ በእራሱ ላይ ለመ
ሸከም በሰው ልጆች መካከል እንደሚመጣ፣
እናም ለዓለም ᵃኃጢያት ክፍያን እንደሚከ
ፍል አውቃለሁ፤ ጌታ እግዚአብሔር ይህን
ተናግሯልና።

፲፮ የኃጢያት ክፍያ መኖሩ አስፈላጊ
ነውና፤ ᵐበዘለአለማዊው አምላክ ታላቅ
ዕቅድ መሰረት ᵃየኃጢያት ክፍያ መኖር
አለበት፤ አለበለዚያ የሰው ዘር ሁሉ መጥ
ፋት እንዳለባቸው የማይቀር ነበር፤ አዎን
ሁሉም ጠማሮች ናቸው፤ አዎን ሁሉም
ᵃᵃወድቀዋልና ጠፍተዋል፣ እናም መፈ
ጸሙ አስፈላጊ ከሆነው ከኃጢያት ክፍያ
በቀር መጥፋት አለባቸው።

፲፯ ታላቅ እና የመጨረሻ ᵐመስዋዕትነት
መኖሩ አስፈላጊ ነውና፤ አዎን፣ የሰውም
ሆነ የእንሰሳ እንዲሁም የማንኛውም አዕ
ዋፍ መስዋዕትነት አይደለም፤ ምክንያቱም
የሰው መስዋዕትነት መሆን አይገባውም፤
ነገር ግን ᵃመጨረሻ የሌለው እንዲሁም ዘለ
አለማዊ ᵃᵃመስዋዕት መሆን ይገባዋል።

፲፰ እንግዲህ ለሌላኛው እንደ ኃጢያቶች
ክፍያ ደሙን መስዋዕት ሊያደርግ የሚችል
ማንም ሰው የለም። እንግዲህ፣ አንድ ሰው
ከገደለ እነሆ ᵐፍፁም የሆነው ህጋችን የወ
ንድሙን ህይወት ያጠፋልን? እኔ ግን አይ
ሆንም እላለሁ።

፲፱ ነገር ግን ህጉ ᵐየገደለውን ሰው ህይወት
ይጠይቃል፤ ስለዚህ ለዓለም ኃጢያት ወሰን
ከሌለው የኃጢያት ክፍያ በስተቀር ሊበቃ
የሚችል ምንም የለም።

፲፲ ስለዚህ፣ ታላቅና የመጨረሻ መስ
ዋዕትነት መኖሩ አስፈላጊ ነው፤ እናም
የደም መፋሰሱ ᵐመቆም መሆን አለበት፣
እንዲሁም መሆኑ አስፈላጊ ነው፤ ከዚያም
ᵃየሙሴ ህግ ይፈፀማል፤ አዎን፣ እያንዳንዱ
ነጥብና ምልክት በሙሉ ይፈፀማል፣ እናም
የትኛውም ሳይከናወን አይቀርም።

፲፳ እናም እነሆ፣ ይህ እያንዳንዱ ትንሽ

፪ ሀ አልማ ፲፯፡ ፲፫–፳፩።
፬ ሀ አልማ ፴፫፡ ፳፫።
፮ ሀ ዮሐ. ፩፡ ፩፣ ፲፬።
፰ ሀ ቅ.መ.መ. መመስከር።
ለ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ዋጋን
መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ።
፱ ሀ አልማ ፲፪፡ ፳፪–፴፫፣
ሙሴ ፮፡ ፳፪።
ለ አልማ ፴፫፡ ፳፪።
ሐ ቅ.መ.መ. የአዳም እና
የሔዋን ውድቀት።
፲ ሀ ሙሴ ፭፡ ፮–፯።
ለ ፪ ኔፊ ፱፡ ፯።
ሐ ቅ.መ.መ. መስዋዕት።
፲፩ ሀ ዘዳግ. ፳፬፡ ፲፮፣
ሞዛያ ፳፱፡ ፳፭።
፲፪ ሀ ቅ.መ.መ. የሞት ቅጣት፤
ግድያ።
፲፫ ሀ ፫ ኔፊ ፱፡ ፲፯፣ ፲፱–፳።
ለ ፫ ኔፊ ፲፭፡ ፭።

ክፍል ወደ ታላቁና የመጨረሻ ᵐመስዋዕት የሚጠቁምበት አጠቃላይ ᵃየህጉ ሐትርጓሜ ነው፤ እናም የታላቁና የመጨረሻ መስዋዕ ትነት የእግዚአብሔር ልጅ ይሆናል፤ አዎን፣ መጨረሻ የሌለውና ዘለዓለማዊ የሆነው።

፲፭ በዚህም በሰሙ ለሚያምኑ ሁሉ ᵐደህ ንነትን ያመጣል፤ የዚህ የመጨረሻው መስ ዋዕት ዓላማ ከፍትህ የሚልቀውን ከአንጀት የሆነን ምህረትን ለማምጣት ነው፤ እንዲ ሁም ለሰዎች በንስሃ እምነት ይኖራቸው ዘንድ መፍትሄ ለማምጣት ነው።

፲፮ እናምእንደዚህም ᵐምህረት ᵃየፍት ህን ፍላጎት ሊያሟላ ይችላል፣ እናም በጠ ባቂ ክንዶቹ ይከባቸዋል፤ እምነትንም ንስሃ በመግባት ያልተለማመደ ሐፍትህ ለሚፈ ልግበት ህግጋት ሁሉ የተጋለጠ ይሆናል፤ ስለዚህ ለንስሃ እምነት ላለው ብቻ ታላቁና ᵐየዘለዓለማዊው ዕቅድ ቤዛነት እንዲመጣ የሚሆነው።

፲፯ ስለዚህ ወንድሞቼ ለንስሃ ᵐእምነታ ችሁን መለማመድ ትጀምሩ ዘንድ፣ በእ ናንተም ላይ ምህረት እንዲኖረው ቅዱስ ስሙን ᵃመጥራት ትጀምሩ ዘንድ እግዚአ ብሔር ለእናንተ ይፍቀድላችሁ፤

፲፰ አዎን፣ ለምህረት ወደ እርሱ ጩኹ፤ ምክንያቱም እርሱ ለማዳን ኃያል ነውና።

፲፱ አዎን፣ ራሳችሁን ዝቅ አድርጉ፣ እናም ወደ እርሱ ፀሎታችሁን አታቋርጡ።

፳ በመስካችሁ ሳላችሁ ወደ እርሱ ጩኹ፤ አዎን በመንጋዎቻችሁ ሁሉ ላይ።

፳፩ በቤታችሁ፣ አዎን፣ በቤተሰዎቻችሁ ላይ፣ በጠዋት፣ በቀን እንዲሁም በምሽት ወደ እርሱ ᵐጩኹ።

፳፪ አዎን፣ የጠላቶቻችሁን ኃይል በመ ቃወም ወደ እርሱ ጩኹ።

፳፫ አዎን፣ ᵐየፅድቅ ሁሉ ጠላት የሆነ ውን ᵃዲያብሎስን በመቃወም ወደ እርሱ ᵐጩኹ።

፳፬ በእርሻችሁ እህሎች ትበለጽጉ ዘንድ ወደ እርሱ ጩኹ።

፳፭ በመስኩ ላይ ያሉት መንጎቻችሁ ይበ ዙላችሁ ዘንድ ስለእነርሱ ጩኹ።

፳፮ ነገር ግን ይህ ብቻም አይደለም፤ ነፍ ሳችሁን ᵐበእልፍኞቻችሁ፤ እናም በሚስ ጥር ቦታዎቻችሁ እንዲሁም በምድረበዳው አፍስሱ።

፳፯ አዎን፣ እናም ወደ ጌታ በማትጮኹ በት ጊዜ፣ ᵐልባችሁ ለደህንነታችሁና፣ ደግሞ በዙሪያችሁ ላሉት ደህንነት ባለማ ቋረጥ በፀሎት ወደ እርሱ በመትጋት ᵃሙሉ ይሁን።

፳፰ እናም አሁን እነሆ፣ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ፣ እንዲህ እላችኋለሁ፤ ይህ ብቻ ነው ብላችሁ አትገምቱ፤ ምክንያቱም ይህ ንን ነገር በሙሉ ካደረጋችሁ በኋላ፣ ᵐየተ ቸገሩትንና፣ የታረዙትን ካልረዳችሁ፣ እናም የታመሙትንና የተሰቃዩትን ካል ጎበኛችሁና፣ እያላችሁ ለሚሹት ካላችሁ ነገር ᵃካላካፈላችሁ—እኔ እንዲህ እላችኋ ለሁ፥ ከእነዚህ ነገሮች የትኛውንም ካላደረ ጋችሁ፣ እነሆ፣ ᵐፀሎታችሁ ᵐከንቱ ነው፣ እናም ለእናንተ የሚጠቅማችሁ ምንም የለም፤ እናንተም እምነትን እንደሚከዱት ግብዞች ናችሁ።

፳፱ ስለዚህ፣ ᵐቸር መሆንን ካላስታወሳ ችሁ፣ (ምክንያቱም ዋጋ ቢስ ነውና) አጣ ሪዎቹ እንደሚጥሉዋቸው እናም በሰዎች እግር እንደሚረገጡ አተላ ናችሁ።

፴ እናም አሁን፣ ወንድሞቼ፣ ብዙ ምስ ክሮችን ከተቀበላችሁ በኋላ፣ ቅዱሳን መጻ

፲፬ ሀ ት. እና ቃ. ፪፴፰፡ ፴፭።
ለ ቅ.መ.መ. የመሴ ህግ።
ሐ አልማ ፴፡ ፫።
፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. ደህንነት።
፲፮ ሀ ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።
ለ ቅ.መ.መ. ፍትህ።
ሐ አልማ ፲፪፡ ፴፪።
መ ቅ.መ.መ. የቤዛነት ዕቅድ።
፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
ለ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
፳፩ ሀ መዝ. ፭፡ ፩–፫፣
፫ ኔፊ ፲፰፡ ፳፩።
፳፫ ሀ ቅ.መ.መ. ጻድቅ፣ ጽድቅ።
ለ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
ሐ ፫ ኔፊ ፲፰፡ ፲፭፣ ፲፰።
፳፭ ሀ ማቴ. ፮፡ ፭–፮።
፲፮ ሀ ቅ.መ.መ. ልብ።
ለ ቅ.መ.መ. ማሰላሰል።
፳፰ ሀ ቅ.መ.መ. ደሀ።
ለ ቅ.መ.መ. ምፅዋት፣ የምፅዋት ስጦታ።
ሐ ማቴ. ፲፭፡ ፯–፰።
መ ሞሮኒ ፯፡ ፮–፰።
፳፱ ሀ ቅ.መ.መ. ልግስና።

ሕፍት እነዚህን ነገሮች እንደሚመሰከሩ ላችሁ እያያችሁ፣ እንድትመጡና ለንስሀ ብቁ የሆነ ᵐፍሬ እንድታመጡ ፍላጎቴ ነው።

፴፩ አዎን፣ እናንተ እንድትመጡና፣ ከእንግዲህ ልባችሁን እንዳታጠጥሩ እፈ ልጋለሁ፤ እነሆም አሁን ᵐየደህንነታችሁ ጊዜና ቀን ነው፤ እናም ስለዚህ ንስሃ የምት ገቡ ከሆነና፣ ልባችሁን የማታጠጥሩ ከሆነ፣ ታላቁ የቤዛነት ዕቅድ በፍጥነት በእናንተ ላይ ይሆናል።

፴፪ እነሆም፣ ይህ ጊዜ ለሰዎች እግዚ አብሔርን ለመገናኘት ᵐየዝግጅት ወቅት ነው፤ አዎን፣ እነሆ የዚህ ህይወት ቀናት ሰዎች ስራቸውን የሚያከናውኑባቸው ቀና ቶች ናቸው።

፴፫ እናም አሁን፣ ለእናንተ ብዙ ምስ ክር እንዳላችሁ ቀደም ሲል እንደተናገር ኩት፣ ስለዚህ እስከመጨረሻው ድረስ ᵐየን ስሃ ቀናችሁን ᵃእንዳታዘገዩ እለምናችኋ ለሁ፤ ለዘለዓለማዊው ህይወት እንድንዘ ጋጅ ከተሰጠን ከዚህ የህይወት ቀን በኋላ፣ እነሆ፣ በዚህ ህይወት ውስጥ ጊዜያች ንን በተሻለ ካልተጠቀምን፣ ከዚያም ስራ ለመስራት የማንችልበት ᵃᵃየጨለማ ᵐምሽት ይመጣል።

፴፬ ወደ አሰቃቂው ᵐሁኔታ ስትመጡም፣ ንስሃ እገባለሁ፣ እናም ወደ አምላኬ እመ ለሳለሁ ለማለት አትችሉም። እንደዚህም ለማለት አትችሉም፤ ከዚህ ህይወት በም ትወጡ ጊዜ እናንተን የእራሱ ያደረገው ይኸው መንፈስ በዘለዓለማዊው ዓለም እና ንተን የእራሱ ለማድረግ ስልጣን ይኖረዋል።

፴፭ እነሆም እስከትሞቱ ድረስ የንስሃ ቀናችሁን የምታዘገዩ ከሆነ፣ እነሆ፣ ለዲያ ብሎስ መንፈስ ᵐተገዢ ትሆናላችሁና፣ የእ ራሱ አድርጎ ᵃያትምባችኋል፤ ስለዚህ የእ ግዚአብሔር መንፈስ ከውስጣችሁ ይወጣ ልና፣ በእናንተ ውስጥ ስፍራ አይኖረውም፣ እንዲሁም ዲያብሎስ በእናንተ ላይ ሁሉም ስልጣን ይኖረዋል፤ እናም የኃጢአተኞች የመጨረሻ ሁኔታ ይህ ነው።

፴፮ እናም ይህን ያወቅሁት ᵐበረከሰ ቤተ መቅደስ እንደማይኖር፣ ነገር ግን ᵃበፃድቃ ኖች ልብ ውስጥ እንደሚያድር ጌታ ስለተ ናገረ ነው፤ አዎን፣ እናም ደግሞ ፃድቃ ኖች በመንግስቱ እንደሚቀመጡ፣ ከዚያም ደግሞ እንደማይወጡ ተናግሯል፤ ነገር ግን በበጉ ደም ልብሳቸው ይጸዳል።

፴፯ እናም አሁን፣ የተወደዳችሁ ወን ድሞቼ፣ እነዚህን ነገሮች እንድታስታ ውሱ እፈልጋለሁ፣ እናም በእግዚአብሔር ፊት በፍርሃት ደኅንነታችሁን ᵐእንድት ፈፅሙና፣ የክርስቶስን መምጣት ከእንግ ዲህ እንዳትክዱ እፈልጋለሁ፤

፴፰ ከእንግዲህ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ᵐእንዳትጣሉም፣ ነገር ግን እንድትቀበሉ ትና፣ ᵃየክርስቶስን ስም በእራሳችሁ ላይ እንድትወስዱት፤ ራሳችሁን እስከትቢያው ድረስ ዝቅ እንድታደርጉና፣ ባላችሁበት ስፍራ ሁሉ በመንፈስና በእውነት እግዚ አብሔርን ᵃᵃእንድታመልኩ፤ እናም በየ ቀኑ በእናንተ ላይ ባደረገው ስለበዛው ምህ ረቱና በረከቱ ᵐበምስጋና እንድትኖሩ እፈ ልጋለሁ።

፴፱ አዎን፣ እናም ደግሞ ወንድሞቼ በዲ ያብሎስ ᵐፈተናም እንዳትወሰዱ፣ እርሱም

፴ ሀ ማቴ. ፫፡፰፤
አልማ ፲፫፡፲፫።
፴፩ ሀ ሮሜ ፲፫፡፲፩–፲፪።
፴፪ ሀ ፪ ኔፊ ፪፡፳፭፤
አልማ ፲፪፡፳፰፤ ፴፪፡፭–፮።
፴፫ ሀ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣ ንስሀ
መግባት።
ለ ሔለ. ፲፫፡፴፰፤
ት.እና ቃ. ፴፭፡፪።
ሐ ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ሞት፣
መንፈሳዊ ጭለማ።
መ ዮሐ. ፱፡፴፤
ት.እና ቃ. ፴፭፡፲፯።
፴፬ ሀ አልማ ፴፡፲፫–፲፰።
፴፭ ሀ ፪ ኔፊ ፳፰፡፲–፲፱፤ ፳፰፡፲።
ለ ፪ ኔፊ ፱፡፱።
፴፮ ሀ ሞዛያ ፪፡፴፯፤
አልማ ፯፡፳፭፤
ሔለ. ፭፡፳፱።
ለ ቅ.መ.መ. ጻድቅ፣ ጽድቅ።
፴፯ ሀ ፊልጵ. ፪፡፲፪።
፴፰ ሀ ቅ.መ.መ. ጸብ።
ለ ሞዛያ ፭፡፳፤
አልማ ፭፡፴፰።
ሐ ቅ.መ.መ. ማምለክ።
መ መዝ. ፳፱፡፴፣
ት.እና ቃ. ፶፱፡፯።
ቅ.መ.መ. አመስጋኝ፣
ምስጋናን፣ ምስጋና
መስጠት።
፴፱ ሀ ቅ.መ.መ. መፈተን፣ ፈተና።

በእናንተ ላይ ስልጣን እንዳይኖረው፣ በመ
ጨረሻው ቀንም በእርሱ ስር እንዳትሆኑ
ያለማቋረጥ ^እንድትፀልዩ እመክራችኋ
ለሁ፤ እነሆ እርሱ ^ምንም መልካም ነገር
ዋጋ አይሰጣችሁምና።

፴፣ እናም አሁን የተወደዳችሁ ወንድሞቼ
ᵐትዕግስት እንዲኖራችሁና፣ ስቃያችሁን
ሁሉ እንድትታገሱ እመክራችኋለሁ፤
እጅግ ድሆች በመሆናችሁ ከአስወጧች
ሁም ላይ አጥብቃችሁ ^አትነቅፉ፣ ያለበ
ለዚያ እንደእነርሱም ኃጢአተኞች ትሆና
ላችሁና፤

፴፪ ነገር ግን ትዕግስት ይኑራችሁ፣ እናም
አንድ ቀን ከስቃያችሁ ሁሉ እንደምታርፉ
ተስፋ በማድረግ ስቃያችሁን ታገሱ።

ምዕራፍ ፴፭

*የቃሉ መሰበክ የዞራማውያንን ተንኮል
ያጠፋል—ወደጌታ የተለወጡትን አስወ
ጡአቸው፣ እነርሱም በኢየርሾን ከአሞ
ንን ሰዎች ጋር ተቀላቀሉ—አልማ በህዝቡ
ክፋት አዘነ። በ፳፱ ም.ዓ. ገደማ።*

፩ አሁን እንዲህ ሆነ አሙሌቅ ንግግሩን
ከጨረሰ በኋላ፣ እራሳቸውን ከህዝቡ ለዩ
እናም ወደ ኢየርሾን ምድር መጡ።

፪ አዎን እናም የቀሩት ወንድሞች ቃሉን
ለዞራማውያን ከሰበኩ በኋላ ደግሞ ወደ
ኢየርሾን ምድር መጡ።

፫ እናም እንዲህ ሆነ በጣም ታዋቂ የሆ
ኑት ዞራማውያን የተሰበኩትን ቃላት በተ
መለከተ እርስ በእርሳቸው ከተመካከሩ በኋላ
ᵐተንኮላቸውን የሚያጠፋባቸው በመሆኑ
በቃሉ ተቆጡ፤ ስለዚህ ቃላቱንም አላደ
መጡትም።

፬ እናም በምድሪቱ ሁሉ የሚኖሩትን
ሰዎች በሙሉ መልዕክት ላኩላቸውና፣ ሰበ
ሰቡአቸው፣ እናም የተነገሩትን ቃላት በተ
መለከተ ከእነርሱ ጋር ተመካከሩ።

፭ እንግዲህ ገዢዎቻቸውና፣ ካህናቶቻ
ቸው፣ እናም መምህራኖቻቸው ለህዝቡ የእ
ነርሱን ፍላጎት እንዲያውቅ አልፈቀዱም፣
ስለዚህ የህዝቡን ሀሳብ በሚስጥር አወቁ።

፮ እናም እንዲህ ሆነ የህዝቡን በሙሉ ሀሳብ
ካወቁ በኋላ፣ በአልማና በወንድሞቹ የተነገ
ሩትን ቃላት የሚደግፉትን ሰዎች ከምድሪቱ
አባረሩአቸው፤ እነርሱም ብዙ ነበሩ፤ እናም
ደግሞ እነርሱ ወደ ኢየርሾን ምድር መጡ።

፯ እናም እንዲህ ሆነ አልማና ወንድሞቹ
ሰበኩላቸው።

፰ እንግዲህ በኢየርሾን በነበሩት በአሞን
ሰዎች ላይ ዞራማውያን ተቆጥተው ነበር፣
እናም የዞራማውያን ዋና ገዢ እጅግ ክፉ ሰው
ስለነበር ከዞራማውያን ምድር ወደ እነርሱ
የመጡትን ከምድራቸው እንዲወጡ በመ
ፈለጉ ለአሞን ህዝብ መልዕክት ላከባቸው።

፱ እናም እርሱ በእነርሱ ላይ በርካታ ማስ
ፈራሪያዎችን ተናገረ። እናም አሁን የአ
ሞን ህዝብ ቃሉን አልፈሩም ነበር፤ ስለዚህ
እነርሱን አላስወጧቸውም ነበር፣ ነገር ግን
ወደእነርሱ የመጡትን ምስኪን ዞራማውያ
ንን በሙሉ ተቀበሉአቸው፤ እናም ᵐተንከባ
ከቧቸውና፣ አለበሱአቸው እንዲሁም የው
ርስ ምድርንም ሰጡአቸው፤ እናም እንደ
ፈለጉት አስተዳደሩአቸው።

፲ እንግዲህ ይህም ዞራማውያን በአሞን
ህዝብ ላይ ለቁጣ እንዲነሳሱ ቀሰቀሳቸው፤
እናም ከላማናውያን ጋር ተቀላቀሉ፣ ደግ
ሞም እነርሱንም በቁጣ ማነሳሳት ጀመሩ።

፲፩ እናም ዞራማውያንና ላማናውያን በአ
ሞን ላይና፣ ደግሞ በኔፋውያን ህዝብ ላይ
ለጦርነት ዝግጅት ጀመሩ።

፲፪ እናም በኔፊ ህዝብ ላይ የመሣፍንቱ
አስራ ሰባተኛው የንግሥ ዘመን ተፈፀመ።

፲፫ እናም የአሞን ህዝብ ከኢየርሾን ምድር
ሸሹና፣ ወደ ሜሌቅ ምድር መጡ፣ እናም
የኔፋውያን ወታደሮች ከላማናውያን ወታ
ደሮች እንዲሁም ከዞራማውያን ወታደሮች

፴፱ሀ ቅ.መ.መ. መጠበቅ፣ ጠባቂ።
ሐ አልማ ፴፡ ፳።
፴፪ሀ ቅ.መ.መ. ትዕግስት።
ለ ት. እና ቃ. ፴፭፡ ፱።
፴፭ ፲ ሀ ቅ.መ.መ. የካህን ተንኮል።
፱ ሀ ሞዛያ ፱፡ ፳፯፤
ቅ.መ.መ. በጎ ድርጊት።

ጋር ይጣሉ ዘንድ የኢየርሾን ምድርን ሰጡ አቸው፤ እናም በመሣፍንቱ አስራ ስምን ተኛ የንግስ ዘመን መጀመሪያ ላይ በላማና ውያንና በኔፋውያን መካከል ጦርነት ተጀ መረ፤ እናም የጦርነታቸው [ሀ]ታሪክም ከዚህ በኋላ ይቀርባል።

፲፬ እናም አልማና፣ አሞን፣ እናም ወንድ ሞቻቸው፣ ደግሞም የአልማ ሁለት ልጆች [ለ]በርካታ ዞራማውያንን ወደ ንስሃው ለማም ጣት በእግዚአብሔር እጅ መገልገያ ከሆኑ በኋላ ወደ ዛራሔምላ ምድር ተመለሱና፣ ወደ ንስሃው የመጡት ብዙዎች ከምድራ ቸው ተሰደዱ፤ ነገር ግን በኢየርሾን ምድር የርስት ሥፍራ ነበራቸው፣ እናም እራሳ ቸውንና፣ ሚስቶቻቸውን፣ እናም ልጆቻ ቸውንና፣ ምድራቸውን ለመከላከል የጦር መሳሪያዎቻቸውን አነሱ።

፲፭ እንግዲህ አልማ በህዝቡ ክፋት፣ አዎን ጦርነትና፣ ደም መፋሰስ፣ እናም በመካ ከላቸው በነበረው ፀብ በማዘኑ፤ በሁሉም ከተሞች እንዲሁም በህዝቡ ሁሉ መካከል ቃሉን በመናገሩ፣ ወይም ቃሉን ለመናገር መልዕክት በመላኩ፤ እናም የህዝቡ ልብ መጠጠሩን በመመልከቱና በቃሉም ጥብ ቅነት የተነሳ [ሐ]መናደድ በመጀመራቸው ልቡ እጅግ አዝኖ ነበር።

፲፮ ስለዚህ ለፅድቅ አስፈላጊ የሆኑትን ነገ ሮች በተመለከተ ለእያንዳንዱ በየግላቸው [መ]ሀላፊነታቸውን ለመስጠት ልጆቹን በአንድ ላይ እንዲሰባሰቡ አደረገ። እናም በአልማ ምዝገባ መሰረት እርሱ የሰጣቸው የትዕዛ ዛት መዛግብት አሉን።

የአልማ ለልጁ ለሔለማን የሰጠው ትዕዛዛት

ምዕራፍ ፴፮ እስከ ፴፯ አጠቃሎ የያዘ።

ምዕራፍ ፴፮

አልማ ለሔለማን መላዕክቱን ከተመለከተ በኋላ ስለመለወጡ መሰከረ—ለተኮነነ ነፍስ ስቃይን ተሰቃየ፤ የኢየሱስን ስም ጠራ፣ እናም ከእግዚአብሔር ተወለደ—ጣፋጩ ደስታ ነፍሱን ሞላው—እግዚአብሔርን የሚያወድሱ ብዛት ያላቸው መላዕክትን ተመለከተ—ብዙ የተለወጡ ቀምሰውታል እናም እርሱ እንደተመለከተው መንፈሳዊ ውን ነገር ተመልክተውታል። በ፳፲ ም.ዓ. ገደማ።

፩ [ሀ]ልጄ ሆይ፣ ቃሌን አድምጥ፤ የእግዚአ ብሔርን ትዕዛዛት እስከጠበቅህ ድረስ በም ድሪቱ ላይ እንደምትበለፅግ ለአንተ እም ላለሁ።

፪ የአባቶቻችንን ምርኮ በማስታወስ እኔ እንዳደረግሁት እንድታደርግ እፈልጋለሁ፤ [ለ]በምርኮ ስለነበሩ [ሐ]ከአብርሃም አምላክና፣ ከይስሀቅ አምላክ፣ እናም ከያዕቆብ አም ላክ በስተቀር ማንም ሊያስለቅቃቸው አይ ችልም፤ እርሱ በእርግጥ ከስቃያቸው አስ ለቅቋቸዋል።

፫ እናም አሁን፣ ልጄ ሔለማን ሆይ፣ እነሆ፣ አንተ ወጣት ነህ፣ እናም ስለዚህ፣ ቃሌን እንድትሰማና ከእኔም እንድትማር እለምንሃለሁ፤ እምነታቸውን በእግዚአብ ሔር ላይ ያደረጉ ሁሉ፣ [መ]በፈተናቸውና፣ በችግራቸው፣ እናም በስቃያቸው እንደ ሚደገፉና፣ በመጨረሻው ቀን [ሠ]ከፍ እን ደሚደረጉ አውቃለሁ።

፬ እናም በራሴ [ረ]እንደማውቀው እንድ ታስብ አልፈልግም—በጊዜያዊው ሳይሆን ነገር ግን በመንፈሳዊው፣ [ሰ]በስጋዊ አዕም ሮዬ ሳይሆን በእግዚአብሔር ነው።

፭ እንግዲህ፣ እነሆ፣ እንዲህ እልሀለሁ፥ [ሸ]ከእግዚአብሔር ባልወለድ ኖሮ እነዚህን

፲፫ *ሀ* አልማ ፴፫፡፲፡።
፲፬ *ለ* አልማ ፴፭፡፮።
፲፭ *ሀ* ቅ.መ.መ. ክህደት።
፲፮ *ሀ* ቅ.መ.መ. መጋቢ፣ መጋቢነት።
፴፮ ፩ *ሀ* ሔለ. ፭፡፱–፲፪።
፪ *ሀ* ሞዛያ ፳፫፡፳፫፣ ፳፬፡፲፮–፳፭።
ለ ዘፀአ. ፫፡፮፣ አልማ ፳፱፡፲፭።
፫ *ሀ* ሮሜ ፰፡፳፰።
ለ ሞዛያ ፳፫፡፳፭–፳፪።
፬ *ሀ* ፩ ቆሮ. ፪፡፲፣ አልማ ፭፡፣ ፴፭–፴፮።
ቅ.መ.መ. እውቀት።
ለ ቅ.መ.መ. ስጋዊ።
፭ *ሀ* ቅ.መ.መ. ዳግመኛ መወለድን፣ ከእግዚአብሔር መወለድ።

ነገሮች ^ባላወቅሁ ነበር፤ ነገር ግን እግዚአ
ብሔር፤ በቅዱስ መልአኩ አንደበት፣ እኔ
ሐብቃት ያለኝ በመሆኔ ሳይሆን፣ እነዚህን
ነገሮች እንዳውቅ አድርጎኛል፤

፤ ከሞዛያ ልጆች ጋር የእግዚአብሔርን
ቤተክርስቲያን ^ለማጥፋት በመፈለግ እሄድ
ነበርና፤ ነገር ግን እነሆ እግዚአብሔር በመ
ንገዳችን እኛን እንዲያቆመን ቅዱስ መል
አኩን ላከ።

፯ እናም እነሆ፣ የነጎድጓድ ድምፅ በሚ
መስልና፣ ምድር ሁሉ በስራችን ^እስክት
ንቀጠቀጥ ተናገረን፤ እናም የጌታ ^ፍርሃት
ስለመጣብን በመሬት ላይ ወደቅን።

፰ ነገር ግን እነሆ፣ ድምፁ እንዲህ አለኝ፥
ተነስ። እናም ተነሳሁና ቆምኩ፣ መልአኩ
ንም ተመለከትኩ።

፱ እናም እርሱ እንዲህ አለኝ፥ ራስህን
ለማጥፋት ከፈለግህም፣ የእግዚአብሔርን
ቤተክርስቲያን ለማጥፋት አትፈልግ።

፲ እናም እንዲህ ሆነ በመሬት ላይ ወደ
ቅሁ፤ እናም ^ለሶስት ቀንና ሌሊት አፌን
ለመክፈትም፣ ሆነ ክንዶቼን ለመጠቀም
አልቻልኩም።

፲፩ እናም መልአኩ ወንድሞቼ ያዳመጡ
ትን፣ ነገር ግን እኔ ላዳምጠው ያልቻልኩ
ትን ከዚህ የበለጡ ነገሮች ተናገረኝ፤ ራስ
ህን ለማጥፋት ከፈለግህም፣ የእግዚአብ
ሔርን ቤተክርስቲያን ከእንግዲህ ለማጥ
ፋት አትፈልግ የሚለውን ቃሉን ስሰማ፣
በታላቁ ፍርሃትና መገረም እጠፋለሁ ብዬ
በመፍራቴ፣ በመሬት ላይ ወደቅሁ፣ እናም
ሌላ ምንም አልሰማሁም።

፲፪ ነገር ግን በስቃይ ^ለዘለዓለም ተጨንቄ
ነበር፣ ነፍሴ በታላቅ ደረጃ ተጨንቃ፣
እናም በኃጢአቶቼ ሁሉ ተሰቃይታ ነበ
ርና።

፲፫ አዎን፣ በሲኦል ህመም ^የተሰቃየ
ሁባቸውን፣ ኃጢአቶቼን እናም ክፋቶ
ቼን ሁሉ አስታውሳለሁ፤ አዎን፣ በአም
ላኬ ላይ ማመፄን፣ እናም ቅዱሳን ትዕዛዛ
ቱን አለመጠበቄን ተመልክቻለሁ።

፲፬ አዎን፣ እናም ብዙዎቼን ልጆቼን
ገድያለሁ፣ ይልቁንም ወደጥፋትም እንዲ
መሩ አድርጌአለሁ፤ አዎን፣ እናም በአጠ
ቃላይ ክፋቶቼ ታላቅ ስለነበሩ፤ ወደ አም
ላኬ በፊቱ ለመቅረብ ያለኝ ሀሳብ በሚያ
ስቸግር ስቃይ ነፍሴን እንድትሰቃይ አደ
ረጋት።

፲፭ ^በስራዬም ሊፈረድብኝ በአምላኬ
ፊት እንዳልቆ ም ዘንድ፣ ^ተወግጄ እና
በነፍስና በስጋዬ ለመጥፋት እንደምችል
አስብበት ነበር።

፲፮ እናም አሁን፣ ለሶስት ቀንና ለሶስት
ሌሊት ^በተኮነነች ነፍስ ህመምም እንኳን
ተሰቃየሁ።

፲፯ እናም እንዲህ ሆነ በጭንቀት በተሰ
ቃየሁ ጊዜ፣ በኃጢአቶቼ ብዛትም በትው
ስታ ^በተሰቃየሁ ጊዜ፣ እነሆ የእግዚአብ
ሔር ልጅ ስለሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ
ተባለው፣ የዓለምን ኃጢያት ለመክፈል
ስለሚመጣው፣ የአባቴን ትንቢት መስ
ማቴን አስታወስኩኝ።

፲፰ እንግዲህ፣ አዕምሮዬ በዚህ ሀሳብ
ላይ በተያዘበት ጊዜ፣ በልቤ እንዲህ በማ
ለት አለቀስኩ፥ የእግዚአብሔር ልጅ የሆ
ንከው ኢየሱስ ሆይ፣ ^ለተማረርኩት፣ እና
በዘለዓለማዊው የሞት ^ሰንሰለት ለተከበብ
ኩት፣ ምህረትህ በእኔ ላይ አድርግልኝ።

፲፱ እናም አሁን፣ እነሆ፣ ይህንን ባሰብኩ
ጊዜ፣ ህመሜን ደግሞ ለማስታወስ አል
ቻልኩም፤ አዎን፣ ከእንግዲህም ወዲያ
በኃጢአቴ ትውስታ ^አልተሰቃየሁም።

፩ ሀ አልማ ፳፤፥ ፳፩–፳፪።
ሐ ቅ.መ.መ. ብቁ፣ ብቁነት።
፤ ሀ ሞዛያ ፳፯፥ ፣።
፯ ሀ ሞዛያ ፳፯፥ ፣፡።
ለ ቅ.መ.መ. ፍርሀት—
እግዚአብሔርን መፍራት።
፣ ሀ ሞዛያ ፳፯፥ ፣፲–፳፫።
፲፪ ሀ ት. እና ቃ. ፣፲፬፥ ፣፩–፣፲፭።
፣፫ ሀ ቅ.መ.መ. በደል።
፣፲፭ ሀ አልማ ፵፩፥ ፫፣
ት. እና ቃ. ፩፥ ፱–፣።
ለ ራዕ. ፤፥ ፣፲–፣፲፣
አልማ ፣፲፪፥ ፣፲፡።
፣፲፮ ሀ ቅ.መ.መ. ኩነኔ።
፣፲፯ ሀ ፪ ቆሮ. ፯፥ ፣።
፣፲፡ ሀ ይህም በታላቅ ሀዘን ማለት
ነው።
ለ ፪ ኔፊ ፱፡ ፴፭፣ ፳፡፡፥ ፳፪፣
አልማ ፣፲፪፥ ፣፲፩፣
ሙሴ ፯፥ ፳፤።
፣፲፱ ሀ ቅ.መ.መ. በደል።

፳ እናም አቤቱ፣ እንዴት ያለ ᵐደስታ ተሰማኝ፤ እናም ምን ዓይነት አስደናቂ ብርሃንን አይቻለሁ፤ አዎን፣ ነፍሴ በህ መም እንደተሰቃየች ሁሉ ታላቅ በሆነም ደስታ ተሞላች!

፳፩ አዎን፣ ልጄ እንዲህ እልሃለሁኝ፥ እንደ እኔ ህመም ሀያልና መሪር የሆነ ምንም ሊኖር አይችልም። አዎን፣ እናም በድጋሚ ልጄ እንዲህ እልሃለሁ፥ በሌላ መልኩ፣ እንደ እኔ ደስታ ሀያልና ጣፋጭ ሊሆን የሚችል ምንም የለም።

፳፪ አዎን፣ አባታችን ᵐሌሂ እንደተመለከ ተው እግዚአብሔር በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ፣ ለአምላካቸው በመዘመር እናም በማወደስ ላይ ባሉት ስፍር ቁጥር በሌላቸው መላዕ ክት ተከቦ የተመለከትኩ መሰለኝ፤ አዎን እናም ነፍሴ በእጅጉ በዚያ ስፍራ መሆንን ናፈቀች።

፳፫ ነገር ግን እነሆ፣ እጆቼና እግሮቼ ᵐብርታትን በድጋሚ አገኙ፣ እናም በእ ግሬ ቆምኩና፣ ለህዝቡም ᶜከእግዚአብ ሔር መወለዴን ገለፅኩ።

፳፬ አዎን፣ እናም ከዚያን ጊዜ እስከአ ሁን ድረስ እንኳን፣ ነፍሳትን ወደ ንስሃ አመጣ ዘንድ፣ እኔ ወደ ᵐቀመስኩት ታላቅ ደስታ እነርሱንም እንዲቀምሱ አመጣቸው ዘንድ፣ እነርሱም ከእግዚአብሔር እንዲወ ለዱ፣ እናም በመንፈስ ቅዱስ ᶜይሞሉ ዘንድ ሳላቋርጥ ሠርቻለሁ።

፳፭ አዎን፣ እናም አሁን እነሆ ልጄ ሆይ፣ ጌታ በስራዬ ፍሬም እጅግ ታላቅ የሆነ ደስ ታን ይሰጠኛል።

፳፮ እኔ እንዳውቀው ባደረገው ᵐቃል የተ ነሳ፣ እነሆ ብዙዎች ከእግዚአብሔር ተወ ልደዋልና፣ እኔ የቀመስኩትን ቀምሰዋል፤ እናም እኔ የተመለከትኩትን ተመልክተ ዋል፤ ስለዚህ የተናገርኳቸውን ነገሮች እኔ እንደማውቅ ያውቃሉ፤ እናም ያለኝ እው ቀት ከእግዚአብሔር ነው።

፳፯ እናም በሁሉም ዓይነት ፈተናና፣ መከራ፣ አዎን፣ በሁሉም ዓይነት ስቃይ ተደግፌአለሁ፤ አዎን፣ እግዚአብሔር ከወህኒ፣ ከእስራትና፣ ከሞት አድኖኛል፤ አዎን፣ እናም እምነቴን በእርሱ አደርጋ ለሁ፣ አሁንም እኔን ᵐያድነኛል።

፳፰ እናም ᵐበክብር ከእርሱ ጋር እንድኖር በመጨረሻው ቀን ᶜእንደሚያስነሳኝ አው ቃለሁ፤ አዎን አባቶቻችንን ከግብፅ ᶜስላ ስወጣና፣ ᵐግብፃውያን በቀይ ባህር እንዲሰ ምጡ ስላደረገ እርሱን ለዘለዓለም አወድሳ ለሁ፤ እናም በኃይሉ ወደ ቃል ኪዳኑ ምድር መርቷቸዋል፤ አዎን፣ እናም በተለያዩ ጊዜ ያት ከባርነትና ከምርኮ አስለቅቋቸዋል።

፳፱ አዎን፣ እናም ደግሞ አባቶቻችንን ከኢየሩሳሌም ምድር አስወጥቷል፤ ደግ ሞም በዘለዓለማዊው ኃይሉ እነርሱን ᵐከባ ርነትና ከምርኮ፣ በየጊዜው እስከ አሁን ድረስም እንኳን፣ አስለቅቋል፤ እናም እኔም ሁልጊዜ ምርኮአቸውን አስታውሳ ለሁ፤ አዎን፣ እናም ደግሞ አንተም ምር ኮአቸውን እኔ እንደአደረግሁት ማስታወስ ይገባሀል።

፴ ነገር ግን እነሆ፣ ልጄ፣ ይህ ብቻም አይ ደለም፤ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት እስከጠ በቅህ ᵐድረስ በምድሪቱ እንደምትበለፅግ እኔ እንደማውቀው ማወቅ አለብህ፤ እናም ደግሞ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት እስካል ጠበቅህ ድረስ ከፊቱ እንደምትወገድ ማወቅ አለብህ። እንግዲህ ይህ በእርሱ ቃል መሰ ረት ነው።

፳ ሀ ቅ.መ.መ. ደስታ።
፳፪ ሀ ፩ ኔፊ ፩፡ ፳።
፳፫ ሀ ሙሴ ፩፡ ፲።
ለ አልማ ፭፡ ፲፬።
ቅ.መ.መ. ዳግመኛ መወለድን፣ ከእግዚአብሔር መወለድ።
፳፬ ሀ ፩ ኔፊ ፳፡ ፲፪፤
ሞዛያ ፬፡ ፲፩።
ለ ፪ ኔፊ ፴፪፡ ፭፤
ቮ ኔፊ ፱፡ ፳።
ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
፳፮ ሀ አልማ ፴፩፡ ፭።
፳፯ ሀ መዝ. ፴፬፡ ፲፯።
፳፰ ሀ ቅ.መ.መ. ክብር።
ለ ቮ ኔፊ ፲፭፡ ፩።
ሐ ዘፀአ. ፲፪፡ ፶፩።
መ ዘፀአ. ፲፡ ፳፯–፳፯።
፳፱ ሀ ሞዛያ ፳፡ ፲፯፤ ፳፯፡ ፲፯፤ አልማ ፭፡ ፭–፮።
፴ ሀ ፪ ኔፊ ፩፡ ፱–፲፩፤ አልማ ፶፡ ፲፱–፳፪።

ምዕራፍ ፴፯

የነሐስ ሰሌዳዎች እናም ሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍት ነፍሳትን ወደ ደህንነት ለማምጣት ተጠበቁ—ያሬዳውያን በክፋታቸው የተነሳ ጠፉ—ሚስጥራዊው መሐላቸው እና ቃል ኪዳናቸው ከህዝቡ መጠበቅ አለበት—በስራችሁም ሁሉ ከጌታ ጋር ተማከሩ—ሊያሆና ኔፋውያንን እንደመራቸው የክርስቶስ ቃልም ሰዎችን ወደ ዘለዓለማዊው ህይወት ይመራቸዋል። በ፫፬ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም አሁን፣ ልጄ ሔለማን፣ ለእኔ [ሀ]በአደራ የተሰጠኝን [ለ]መዛግብት እንድት ወስድልኝ አዝሃለሁ፤

፪ እናም ደግሞ በኔፊ ሰሌዳ ላይ ያለውን የዚህን ህዝብ ታሪክ እኔ እንዳደረግሁት እንድትጠብቅ አዝሀለሁ፣ እናም እኔ የጠበቅኋቸውን እነዚህን ቅዱስ ነገሮች ሁሉ እኔ እንደጠበቅኋቸው አድርግ፤ ምክንያቱም እነዚህ የተጠበቁት [ሐ]ለመልካም ዓላማ ነውና።

፫ እናም እነዚህን ፅሁፎች የያዙት፣ የቅዱሱን መጻሕፍት ታሪክ የያዙትን፣ የጥንት ቅድመ አባቶቻችንን የትውልድ ሀረግ ከመጀመሪያው ጀምሮ የያዙትን፣ እነዚህ [መ]የነሐስ ሰሌዳዎች—

፬ እነሆ፣ እነዚህ ነገሮች ተጠብቀው ከአንዱ ትውልድ ወደሌለኛው እንዲተላለፉ፣ እናም ለሁሉም ሀገር፣ ነገድ፣ ቋንቋ፣ እና ህዝብ እስኪደርሱ በውስጣቸው ያለውን [ሠ]ሚስጥር እንዲያውቁ በጌታ እጅ መቀመጥ እንዳለባቸው በአባቶቻችን ተተንብዮአል።

፭ እናም አሁን እነሆ፣ ከተጠበቁም ብሩህነታቸውን ይዘው መቀጠል አለባቸው፤ አዎን፣ እናም እነርሱም፣ አዎን፣ ደግሞም ቅዱስ ፅሑፍ የሆኑትን የያዙ ሰሌዳዎችም ብሩህነታቸውን ይዘው ይቀጥላሉ።

፮ አሁን ይህ በእኔ ውስጥ ያለ [ረ]ሞኝነት ነው በማለት ትገምት ይሆናል፤ ነገር ግን እነሆ እንዲህ እልሀለሁ፥ [ሰ]በትንሽና በቀላል ነገሮች ታላቅ ነገሮች ተፈፅመዋል፤ እናም ቀላል መንገዶች ብዙውን ጊዜ ጥበበኞችን ያሳፍራሉ።

፯ እናም ጌታ እግዚአብሔር ታላቁንና ዘለዓለማዊ አላማውን ለማምጣት በእነዚህ [ሸ]መንገዶች ይሰራል፤ እናም በጣም [ቀ]ቀላል በሆነ መንገድ ጌታ ጥበበኞችን ያሳፍራልና፣ የብዙ ሰዎችን ነፍስ ወደ ደህንነት ያመጣል።

፰ እናም አሁን፣ እስከአሁን ድረስ እነዚህ ነገሮች እንዲጠበቁ በእግዚአብሔር ጥበብ ሆኖ ቆይቷል፤ እነሆ፣ የዚህን ህዝብ ትዝታ [በ]አስፍተዋል፣ አዎን፣ እናም ብዙ የጎዳና ዎቻቸውን ተሳሳችነት አሳምነዋል፣ እናም ለነፍሳቸው ደህንነትም እግዚአብሔርን እንዲያውቁ አድርጓቸዋል።

፱ አዎን፣ እኔ እንዲህ እላችኋለሁ፥ በእነዚህ ሰሌዳዎች ላይ በሚገኙት እነዚህ መዝገቦች ውስጥ ከሚይዟቸው በእነዚህ ነገሮች [ተ]ባይሆን ኖሮ አሞንና ወንድሞቹ ብዙ ሺህ ላማናውያንን የአባቶቻቸው ወግ የተሳሳተ እንደሆነ [ቀ]ሊያሳምኑአቸው አይችሉም ነበር፤ አዎን፣ እነዚህ ታሪኮች እና [ሐ]ቃላቶቻቸው ወደንስሃ አመጡአቸው፤ ይህም ማለት፣ ጌታ አምላካቸውን እንዲያውቁ እናም በአዳኛቸው በኢየሱስ ክርስቶስ ሐሴትን እንዲያደርጉ አደረጉአቸው።

፲ እና፣ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ እነዚህን፣ አዎን፣ እናም ደግሞ፣ አሁን በኃጢያትና በክፋት ልባቸውን የሚያጠጥሩትን አንገተ ደንዳና የሆኑ ኔፋውያን ወንድሞቻችንን

፴፯ ፩ [ሀ] ሞዛያ ፳፰፡፡
[ለ] አልማ ፴፭፡፪–፳።
፪ [ሀ] ኢኖስ ፩፡ ፲፫–፲፰፣ ቃላት ፩፡ ፯–፲፩፣ አልማ ፴፯፡ ፱–፲፪።
፫ [ሀ] ፩ ኔፊ ፭፡ ፲–፲፱።
[ለ] ቅ.መ.መ. የህስ ሰሌዳዎች።
፬ [ሀ] ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ሚስጥሮች።
፭ [ሀ] ፩ ቆሮ. ፪፡ ፲፡
[ለ] ፩ ኔፊ ፲፯፡ ፳፰–፳፱፣ ት. እና ቃ. ፳፡ ፴፫፣ ፲፳፫፡ ፲፭–፲፯።
፯ [ሀ] ኢሳ. ፶፭፡ ፰–፱።
[ለ] ፪ ነገሥ. ፭፡ ፩–፲፡
፰ [ሀ] ፪ ጢሞ. ፫፡ ፲፭–፲፯፣ ሞዛያ ፩፡ ፫–፭።
፱ [ሀ] ሞዛያ ፩፡ ፭።
[ለ] አልማ ፲፰፡ ፴፯፣ ፳፪፡ ፲፪።
[ሐ] ቅ.መ.መ. ወንጌል።

አዳኙን ወደ ማወቅ እንደሚያመጡ ማን ያውቃል?

፲፩ አሁን እነዚህ ሚስጥሮች ሙሉ በሙሉ ለእኔ አልታወቁኝም፤ ስለዚህ ይበልጥ ከመ ናገር ልቆጠብ።

፲፪ እናም በእግዚአብሔር ለሚታወቀው ዓላማ፣ ለመልካም ዓላማ ተጠበቁ ብቻ ካልኩኝ ይበቃኛል፤ ምክንያቱም በስራ ዎቹ ሁሉ በጥበብ [ሀ]ይመክራልና፣ እናም ጎዳናው ቀጥተኛ መንገዱም [ለ]አንድ ዘለዓ ለማዊ ዙሪያ ነው።

፲፫ አስታውስ ልጄ ሔለማን ሆይ፣ የእግ ዚአብሔር ትዕዛዛት እንዴት [ሐ]ጥብቅ እን ደሆኑ አስታውስ። እናም እርሱ እንዲህ ብሏል፥ ትዕዛዛቴን [ለ]ከጠበቅህ በምድሪቱ ላይ [መ]ትበለፅጋለህ—ነገር ግን ትዕዛዛቱን ካልጠበቅህ ከፊቱ ትለያለህ።

፲፬ እናም ልጄ አሁን ጌታ ቅዱስ የሆኑ ትን፣ [ሀ]ቅዱስ አድርጎ የጠበቃቸውን እናም ደግሞ ለወደፊቱም ትውልድም ኃይሉን ያሳይበት ዘንድ [ለ]ለመልካም ዓላማው የሚ ጠብቃቸውን እነዚህን ነገሮች [ሐ]በአደራ እን ደሰጠህ አስታውስ።

፲፭ እናም አሁን እነሆ፣ በትንቢት መን ፈስ እናገርሃለሁ፤ የእግዚአብሔርን ትዕ ዛዛት የምትተላለፍ ከሆነ፣ እነሆ፣ እነዚህ ቅዱስ የሆኑት ነገሮች በእግዚአብሔር ኃይል ይወሰዱብሃል፣ እናም በንፋሱ ፊት እንዳለ ገለባ እንዲያበጥርህ ለሰይጣን ይሰጥሃል።

፲፮ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ከጠበቅህ፣ እናም በእነዚህ ቅዱስ ነገሮች እግዚአብሔር ባዘዘህ መሰረት ከሰራህ (በም ታደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ወደ ጌታ አቤት እንድትል ይገባልና) እነሆ ከአንተ [ሀ]ሊወ ስድብህ የሚችል ምንም ኃይል፣ የምድ ርም ሆነ የሲኦል፣ አይኖርም፣ ምክንያቱም

እግዚአብሔር ቃሉን ሁሉ ይፈፅም ዘንድ ኃያል ነውና።

፲፯ ለአንተ የገባውን ቃል ኪዳን በሙሉ ይፈፅማልና፣ ለአባቶቻችን የገባውን ቃል ኪዳንም ይፈፅማልና።

፲፰ ኃይሉን ለሚመጣው ትውልድ ያሳይ ዘንድ፣ እነዚህን ነገሮች ለመልካም ዓላማው [ሀ]እንደሚጠብቃቸው ቃል ኪዳን ገብቶላ ቸዋልና።

፲፱ እናም አሁን እነሆ፣ [ሀ]ብዙ ሺህ ላማና ውያንን እውነትን እንዲያውቁ በመመለስ አንዱን ዓላማውን ፈፅሟል፤ በእነርሱም ኃይሉን አሳይቷል፤ እናም [ለ]ለሚመጣው ትውልድም ደግሞ አሁንም በእነርሱ ኃይ ሉን ያሳያል፤ ስለዚህ እነዚህ ነገሮች ይጠ በቃሉ።

፳ ስለዚህ ልጄ ሔለማን ቃሌን በመፈፀም ትጉህ እንድትሆን እናም እንደተፃፉት የእ ግዚአብሔርን ትዕዛዛት በመጠበቅ ትጉህ እንድትሆን አዝሃለሁ።

፳፩ እናም አሁን፣ [ሀ]ሀያ አራቱን ሰሌዳዎች በተመለከተ፣ ሚስጥሮችንና፣ የጨለማው ስራ፣ እናም የእነርሱን [ለ]ሚስጥራዊ ስራ፣ ወይም የጠፉት ሰዎች የሚስጥር ስራ ለዚህ ህዝብ ይገለጥ ዘንድ እንድትጠብቃቸው እናገራለሁ፤ አዎን፣ ግድያቸውን ሁሉና፣ ስርቆታቸውንና፣ ዝርፊያቸውንና፣ ክፋ ታቸውንና፣ እርኩሰታቸውን ሁሉ ለዚህ ህዝብ ይገልጡ ዘንድ፤ አዎን፣ እናም እነ ዚህን [መ]መተርጎሚያዎች አስቀምጥ።

፳፪ እነሆም፣ ጌታ ይህ ህዝብ በጨለማው መሥራት፣ አዎን፣ ሚስጥራዊ ግድያንና እርኩሰትን፣ ሲጀምር ተመለከተ፤ ስለዚህ ጌታ እንዲህ ይላል፥ ንስሃ የማይገቡ ከሆነ ከምድር ገፅ ይጠፋሉ።

፳፫ እናም ጌታ እንዲህ ይላል፥ ለአገልጋዬ

፲፪ ሀ ፪ ኔፊ ፱፡ ፳፰፣ ያዕቆ. ፩፡ ፲። ለ ፩ ኔፊ ፣ ፣ ፲፱፣ አልማ ፯፡ ፳። ፲፫ ሀ ፪ ኔፊ ፱፡ ፣ ለ አልማ ፱፡ ፲፫፣ ፫ ኔፊ ፭፡ ፳፪።

ሐ ሞዛያ ፩፡ ፯፣ አልማ ፣ ፳። ፲፬ ሀ ቅ.መ.መ. ቅዱስ። ለ ፩ ኔፊ ፱፡ ፣ ሐ ት.እና ቃ. ፣ ፭። ፲፯ ሀ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡ ፣ ፲፱። ፲፰ ሀ ት.እና ቃ. ፭፡ ፱።

፲፱ ሀ አልማ ፳፫፣ ፭። ለ ኢኖስ ፩፡ ፲፣ ሞር. ፣ ፡ ፣ ፳፩ ሀ ኤተር ፩፡ ፩–፭። ለ ቅ.መ.መ. የሚስጥር ስብሰባ። ሐ ቅ.መ.መ. ኡሪም እና ቱሚም።

ጋዜሌም፣ በጨለማ በብርሃን የሚያንፀባርቀውን [ሀ]ድንጋይ አዘጋጅለታለሁ፤ እኔን ላገለገሉኝም እገልፅላቸዋለሁ፣ የወንድሞቻቸውንም ስራ፣ አዎን፣ ሚስጥራዊ ስራቸውን፣ የጨለማ ስራቸውንና ክፋታቸውን፣ እናም እርኩሰታቸውን አሳያቸዋለሁ።

፳፬ እናም አሁን፣ ልጄ፣ እነዚህ ተርጓሚዎች ጌታ እንዲህ በማለት የተናገረውን ቃላት ይፈፀሙ ዘንድ ተዘጋጅተዋል፥

፳፭ ሚስጥራዊ ስራዎቻቸውን እና እርኩሰታቸውን ከጨለማው ወደ ብርሃኑ [ሀ]አመጣዋለሁ፤ እናም ንስሃ ካልገቡ ከምድረ ገፅ [ለ]አጠፋቸዋለሁ፤ እናም ሁሉ ከዚህ በኋላ ምድሪቷን የራሳቸው ለሚያደርጉ ሀገሮች ሁሉ ሚስጥራቸውንና እርኩሰታቸውን ወደ ብርሃን አመጣለሁ።

፳፮ እናም አሁን፣ ልጄ፣ እነርሱ ንስሃ እንዳልገቡ እናያለን፤ ስለዚህም ጠፍተዋል፤ እናም እስከዚህ ድረስ የእግዚአብሔር ቃል ተፈፅሟል፤ አዎን ሚስጥራዊው እርኩሰታቸው ከጨለማው ወጥቷል እናም እኛ እንድናውቀው ተደርጓል።

፳፯ እናም እንግዲህ፣ ልጄ፣ መሃላዎቻቸውን፣ ቃል ኪዳናቸውንና፣ ሚስጢራዊ የሆነውን የእርኩሰታቸውን ስምምነት ሁሉ እንድትጠብቅ አዝሀለሁ፤ አዎን እናም [ሀ]ምልክቶቻቸውንና አስደናቂ ነገሮቻቸውን ሁሉ እንዳያውቋቸው ከእነዚህ ሰዎችም ትጠብቃለህ፤ አለበለዚያ በጨለማው ውስጥ እነርሱ ይወድቁ ይሆናል፣ እንዲሁም ሊጠፉ ይችላሉና።

፳፰ እነሆ የጨለማ ሠራተኞቹም በክፋት ሙሉ በሙሉ ባደጉ ጊዜ በእግዚአብሔር ኃይል መሰረት የጭለማ ስራን በሚሰሩት ላይ ሁሉ ጥፋት እንደሚመጣባቸው በምድሪቱ ላይ ሁሉ [ሀ]እርግማን አለ፤ ስለሆነም እነዚህ ሰዎች እንዳይጠፉ እመኛለሁ።

፳፱ ስለዚህ ከዚህ ህዝብ ይህንን [ሀ]የመሃላቸውንና የቃል ኪዳናቸውን ሚስጥራዊ እቅድ ትጠብቃለህ፣ እናም ክፋታቸውንና፣ ግድያቸውን፣ እንዲሁም እርኩሰታቸውን ብቻ ለእነርሱ እንዲታወቁ አድርግ፤ እናም እንደዚህ ዓይነቱን ኃጢያትና፣ እርኩሰት፣ እንዲሁም ግድያ [ለ]እንዲጠሉ አስተምራቸው፤ እናም ደግሞ ይህ ህዝብ በክፋቱና በእርኩሰቱ፣ እንዲሁም በመግደሉ ምክንያት እንደጠፉ አስተምራቸው።

፴ እነሆም ስለኃጢአታቸው ለመናገር ከእነርሱ መካከል የመጡትን የጌታን ነቢያት በሙሉ ገደሉአቸው፤ እናም የተገደሉት ደም በገደሉአቸው ላይ ወደ ጌታ አምላካቸው ለበቀል ጮኸ፤ እናም የእግዚአብሔር ፍርድ በጨለማው ሰራተኞችና፣ በሚስጥራዊው ሴራዎች ላይ እንደዚህ መጣ።

፴፩ አዎን፣ እናም ሁሉም በክፋት ከማደጋቸው በፊት ንስሃ ካልገቡ በስተቀር፣ በጨለማው ሰራተኞች፣ እናም በሚስጥራዊው ሴራዎች ላይ ለጥፋትም እንኳን ምድሪቱ ለዘለዓለም ረገማት።

፴፪ እናም አሁን፣ ልጄ፣ የተናገርኩህን ቃላት አስታውስ፤ ሚስጥራዊ ዕቅድን ለህዝቡ በአደራ ለመስጠት አትመን፣ ነገር ግን በኃጢያት እና በክፋት ላይ ዘለዓለማዊ [ሀ]ጥላቻን አስተምራቸው።

፴፫ ንስሃን እናም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እምነትን [ሀ]ስበክላቸው፤ እራሳቸውን ዝቅ እንዲያደርጉና፣ [ለ]የዋህ፣ እናም በልባቸው ትሁት እንዲሆኑ አስተምራቸው፤ ማንኛውንም የዲያብሎስ [ሐ]ፈተና በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ባላቸው እምነት እንዲቋቋሙ አስተምራቸው።

፴፬ ለመልካም ስራ በጭራሽ እንዳይታክቱ፣ ነገር ግን የዋህ፣ እናም በልባቸው ትሁት እንዲሆኑ አስተምራቸው፤ ምክንያቱም እንደ እነዚህ ያሉት ለነፍሳቸው [ሀ]ዕረፍትን ያገኛሉና።

፳፬ ሀ ሞዛያ ፰፥ ፲፫።
፳፭ ሀ ት. እና ቃ. ፹፰፥ ፻፰–፻፲።
ለ ሞዛያ ፳፩፥ ፳፮።
፳፯ ሀ ሔለ. ፮፥ ፳፪።
፳፰ ሀ አልማ ፵፭፥ ፲፮፤
ኤተር ፪፥ ፯–፲፪።
፳፱ ሀ ሔለ. ፮፥ ፳፭።
ለ አልማ ፲፫፥ ፲፪።
፴፪ ሀ ፪ ኔፊ ፬፥ ፴፮።
፴፫ ሀ ቅ.መ.መ. መስበክ።
ለ ቅ.መ.መ. ገር፣ ገርነት።
ሐ ቅ.መ.መ. መፈተን፣ ፈተና።
፴፬ ሀ መዝ. ፴፯፥ ፬–፯፤
ማቴ. ፲፩፥ ፳፰–፴።

፴፩ ልጄ ሆይ፣ አስታውስ፣ እናም በጎል ማሳነትህ ዘመን ᵐጥበብን ተማር፤ አዎን፣ በወጣትነትህ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት መጠበቅን ተማር።

፴፪ አዎን፣ እናም ለድጋፍህ ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ᵐጩህ፤ አዎን፣ ስራህ ሁሉ ለጌታ ይሁን፣ እናም ወደ የትኛውም ሥፍራ ብትሄድ በጌታ ይሁን፤ አዎን፣ ሀሳብህ ሁሉ በጌታ የተመራ ይሁን፤ አዎን የልብህ ዝንባሌ ለዘለዓለም በጌታ ላይ ይሁን።

፴፫ በስራዎችህ ሁሉ ከጌታ ጋር ᵐተማከር፣ እናም ለአንተ ጥቅም ይመራሃልና፤ አዎን፣ በምሽት በምትተኛበት ጊዜ በእንቅልፍህ ይጠብቅህ ዘንድ በጌታ ተኛ፤ እናም ጠዋት ከመኝታህ በምትነቃበት ጊዜ ልብህ ሁሉ እግዚአብሔርን ᵃበማመስገን ይሞላ፤ እናም እነዚህን ነገሮች የምታደርግ ከሆነ፣ በመጨረሻው ቀን ከፍ ትደረጋለህ።

፴፬ እናም አሁን ልጄ፣ አባቶቻችን ኳስ ወይንም ጠቋሚ ብለው ስለሚጠሩት፣ ወይም በትርጉም አቅጣጫን የሚጠቁም መሳሪያ የሆነው፣ አባቶቻችን ᵐሊያሆና ብለው የሚጠሩትን በሚመለከት በመጠኑ የምናገረው አለኝ፤ እናም እርሱንም ጌታ አዘጋጅቶታል።

፴፭ እናም እነሆ፣ እንደዚህ አይነት አስደናቂ የእጅ ስራን ሊሰራ የሚችል ማንም ሰው የለም። እናም እነሆ፣ አባቶቻችን በምድረበዳው ውስጥ እንዲጓዙበት አቅጣጫን ለማሳየት ተዘጋጅቶ ነበር።

፴ እናም ይህም ይሰራ የነበረው በእግዚአብሔር ባላቸው ᵐእምነት መሰረት ነበር፤ ስለዚህ፣ እግዚአብሔር እንዝርቱ የሚሄዱበትን አቅጣጫ እንዲያመለክት እንደ ሚያደርገው ለማመን እምነት በነበራቸው መጠን፣ እነሆ ተከናውኖላቸዋል፤ ስለዚህ ይህ ተአምራት ነበራቸው፣ እናም ደግሞ ብዙ ከቀን ቀን በእግዚአብሔር ኃይል የነበሩ ሌሎች ታምራቶች ነበሯቸው።

፴፩ ይሁን እንጂ፣ እነዚያ ታምራቶች ᵐበትንሽ ነገር የተደረጉ ቢሆንም ድንቅ ስራዎችን አሳይተዋቸው ነበር። እነርሱ ሰነፍ ነበሩ፣ እናም እምነታቸውንና ትጋታቸውን መለማመድ ረሱ፣ እናም እነዚያ ድንቅ ስራዎች ቆሙና፣ በጉዞአቸውም ወደፊት አልቀጠሉም፤

፴፪ ስለዚህ፣ በምድረበዳው ውስጥ ቆዩ፣ እንዲሁም ቀጥታውን መንገድ አልተጓዙም፣ እናም በመተላለፋቸው ምክንያት በረሃብና በጥም ተሰቃዩ።

፴፫ እናም አሁን፣ ልጄ፣ እነዚህ የነገሮች ጥላ የሌላቸው አለመሆናቸውን እንድትገነዘብ እፈልጋለሁ፤ አባቶቻችን ለዚህ አቅጣጫ ጠቋሚ መሳሪያ ትኩረትን ላለመስጠት ሰነፍ በሆኑ ጊዜ (አሁን እነዚህ ነገሮች ጊዜያዊ ነበሩ) አልበለፀጉም፤ መንፈሳዊ ለሆኑትም ነገሮች ቢሆን እንዲሁ ነው።

፴፬ እነሆም አባቶቻችንም ወደ ቃል ኪዳን ምድር በቀጥተኛው መንገድ የሚያመራቸውን ኮምፓስ መከተሉ አይነት ወደ ዘለዓለማዊው ደስታ የሚያመራ ቀጥተኛው መንገድ የሆነውን ᵐየክርስቶስን ቃል መቀበልም ነው።

፴፭ እናም አሁን እንዲህ እላለሁ፣ ለዚህ ነገር ምሳሌ የለምን? በእርግጥ ይህ አመልካች ጎዳናውን ተከትሎ አባቶቻችንን ወደ ቃል ኪዳኑ ምድር እንዳመጣ፣ የክርስቶስንም ቃላት ከተከተልናቸው ከዚህ ከሀዘን ሸለቆ እጅግ ወደ ተሻለው የቃል ኪዳን ምድር ይወስደናል።

፴፮ ልጄ ሆይ፣ ᵐመንገዱ ቀላል በመሆኑ ᵃሰነፍ አንሁን፤ ለአባቶቻችንም እንዲሁ ነበርና፣ ለእነርሱም የሚመለከቱት ከሆነ

፴፩ ᵐ ቅ.መ.መ. ጥበብ።
፴፮ ᵐ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
፴፮ ᵃ ያዕቆ. ፩፡፲፣
ት. እና ቃ. ፫፡፴።
ለ ት. እና ቃ. ፴፮፡፴፪።
፴፯ ᵃ ፩ ኔፊ ፲፮፡፲፣ ፲፰፡፲፪፣
ት. እና ቃ. ፲፮፡፩።
፴ ᵃ ፩ ኔፊ ፲፩፡፳፯፤
ᵇ ᵃ ፩ ኔፊ ፲፩፡፳፰፣ ፳፱፣
ᶜ ᵃ ፩ ኔፊ ፲፩፡፳፱፣ ፴፡
ᵈ ᵃ አልማ ፴፯፡፮–፯።
፴፩ ᵃ መዝ. ፻፲፱፡፻፭፣
ᵇ ᵃ ፩ ኔፊ ፲፩፡፳፭፣
ᶜ ᵃ ሔለ. ፫፡፳፱–፴።
ᵈ ᵃ ዮሐ. ፲፡፡–፭፣
ᵇ ᵃ ፩ ኔፊ ፱፡ ፴፭፣
ᶜ ᵃ ፴፭፡ ፲፯–፳፭፣
ት. እና ቃ. ፳፴፪፡ ፳፱፣ ፳፭።
ለ ᵃ ፩ ኔፊ ፲፯፡ ፴–፴፩።

ሐበህይወት ይቆዩ ዘንድ ለዚህ ተዘጋጅቶላ
ቸው ነበርና፤ ለእኛም ቢሆን እንዲሁ ነው።
መንገዱ ተዘጋጅቷል፣ እናም የምንመለከት
ከሆነ ለዘለዓለም እንኖራለን።

፴፯ እናም አሁን፣ ልጄ፣ እነዚህን ቅዱስ
ነገሮች ጠብቅ፤ አዎን፣ ወደ እግዚአብሔር
ተመልከትና ኑር። ወደዚህ ህዝብ ሂድና፣
ቃሉን ተናገር፣ እናም ንቃ። ልጄ ደህና
ሰንብት።

አልማ ለልጁ ለሺብሎን የሰጠው ትዕዛዛት

ምዕራፍ ፴፰ አጠቃሎ የያዘ።

ምዕራፍ ፴፰

*ሺብሎን ለፅድቅነት ምክንያት ስደት ደረ
ሰበት—ደህንነት የዓለም ህይወትና ብርሃን
በሆነው በክርስቶስ ነው—ስሜቶቻችሁን
በሙሉ ተቆጣጠሩ። በ፳፲፩ ም.ዓ. ገደማ።*

፩ ልጄ፣ ቃሌን አድምጥ፣ ለሔለማን
እንኳን እንደተናገርኩ ለአንተም ተናግሬ
አለሁ፣ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት እስከ
ጠበቅህ ድረስ በምድሪቱ ላይ ትበለፅጋ
ለህ፤ እናም የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት እስ
ካልጠበቅህ ድረስ ከፊቱ እንድትለይ ትደ
ረጋለህ።

፪ እናም አሁን፣ ልጄ፣ ለእግዚአብሔር
ባለህ ፅኑነት፣ እናም ታማኝነት፣ በአንተ
ታላቅ ደስታ እንደሚኖረኝ አምናለሁ፤
በአምላክህ በወጣትነትህ ተስፋ መጣልህን
በመጀመርህ፣ ትዕዛዛቱን በመጠበቅ [ሀ]እንደ
ምትቀጥል ተስፋ አደርጋለሁ፤ ምክንያቱም
እስከመጨረሻው [ለ]የፀና የተባረከ ነውና።

፫ ልጄ፣ እኔ እንዲህ እልሀለሁ፡ [ሐ]በዞራማ
ውያን መካከል በታማኝነትህ፣ እናም በት
ጋትህና፣ በፅናትህ እንዲሁም በታጋሽነትህ
የተነሳ በአንተ ታላቅ ደስታን አግኝቻለሁ።

፬ አንተ ታስረህ እንደነበርህ አውቃለሁ፤
አዎን፣ እናም አንተ ለቃሉ ስትል በድንጋይ
መወገርህን አውቃለሁ፤ ጌታም [መ]ከንተ ጋር
በመሆኑ እነዚህን ነገሮች ሁሉ [ሠ]በትዕግስት
ጸንተህል፤ እናም አሁን ጌታ እንዳስለቀቀህ
አንተም ታውቃለህ።

፭ እናም እንግዲህ ልጄ፣ ሺብሎን፣
[ረ]እምነትህን በእግዚአብሔር ላይ እስካደ
ረግህ ድረስ [ሰ]ከፈተናህና ከችግርህ፣ እናም
[ሸ]ከስቃይህ እንደዚሁ እንደምትላቀቅና፣
በመጨረሻው ቀን ከፍ እንደምትደረግ እን
ድታስታውስ እፈልጋለሁ።

፮ እንግዲህ፣ ልጄ፣ እነዚህን ነገሮች
በራሴ እንዳወቅኋቸው እንድታስብ አል
ፈልግም፤ ነገር ግን በውስጤ ያለው የእግ
ዚአብሔር መንፈስ እነዚህን ነገሮች እንዳ
ውቅ አደረገኝ፤ ምክንያቱም [ቀ]ከእግዚአብ
ሔር ባልወለድ ኖሮ እነዚህን ነገሮች ባላ
ወቅሁ ነበር።

፯ ነገር ግን እነሆ፣ ጌታ በታላቅ ምህረቱ
በዚህ ህዝብ መካከል [በ]የጥፋት ስራን እንዳ
ቆም እንዲነግረኝ [ተ]መልአኩን ላከ፤ አዎን፣
እናም መልአኩን ፊት ለፊት ተመለከትኩ
ትና፣ ተናገረኝ፣ ድምፁም እንደነጎድጓድ
ነበር፣ እናም ምድሪቷን በሙሉ አንቀጠ
ቀጣት።

፰ እናም እንዲህ ሆነ ለሶስት ቀንና ሌሊት
ነፍሴ በመሪር ህመምና ስቃይ ውስጥ ነበ
ረች፤ እናም ወደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ
ለምህረት እስከምጮህ ድረስ ለኃጢአቴ
[ተ]ስርየትን በጭራሽ አላገኘሁም ነበር። ነገር
ግን እነሆ፣ ወደ እርሱ ጮህኩና፣ ለነፍሴም
ሰላምን አገኘሁ።

፴፯ሐ ዮሐ. ፲፩፡ ፳፭፤
ሔለ. ፰፡ ፲፭፤
ቮ ኔፊ ፲፭፡ ፱።
፴፰ ፪ ሀ አልማ ፰፣ ፡ ፩–፪።
ለ ፪ ኔፊ ፴፩፡ ፲፭–፳፤
ቮ ኔፊ ፲፭፡ ፱፤ ፳፯፡ ፮፣
፲፯–፲፯።
ቮ ሀ አልማ ፴፩፡ ፯።
፬ ሀ ሮሜ ፰፡ ፴፭–፴፱።
ለ ቅ.መ.መ. ትዕግስት።
፭ ሀ አልማ ፴፯፡ ፳፯።
ቅ.መ.መ. መታመን።
ለ ማቴ. ፲፩፡ ፳፰–፴።
ሐ ት.እና ቃ. ፲፡ ፰፣
፲፳፩፡ ፯–፰።
፮ ሀ አልማ ፴፯፡ ፳፯፤
ት.እና ቃ. ፭፡ ፲፯።
ቅ.መ.መ. ዳግመኛ
መወለድ፣ ከእግዚአብሔር
መወለድ።
፯ ሀ አልማ ፳፯፡ ፲፯–፲፰፤
፴፯፡ ፯–፲፩።
ለ ሞዛያ ፳፯፡ ፲፩–፲፯።
፰ ሀ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ስርየት።

፱ እናም አሁን ልጄ፣ በክርስቶስ ብቻ ካልሆነ በቀር መዳን የሚቻልበት ᵐሌላ መን ገድ እንደሌለ፣ ከእኔ ትማር ዘንድ ጥበብ ንም እንድትማር ይህን ነግሬሀለሁ። እነሆ፣ እርሱ የዓለም ህይወትና ᵃብርሃን ነው። እነሆ፣ እርሱ የእውነትና የፅድቅ ቃል ነው።

፲ እናም አሁን፣ ቃሉን ማስተማር እን ደጀመርህ ደግሞም ማስተማርን እንድት ቀጥል እፈልጋለሁ፤ እናም በሁሉም ነገር ትጉህና ራስህን የምትቆጣጠር እንድትሆን እፈልጋለሁ።

፲፩ አንተ በኩራት እንዳልተሞላህ አረጋ ግጥ፤ አዎን፣ በራስህ ጥበብም ሆነ በጉል በትህ ᵐእንደማትመካ አረጋግጥ።

፲፪ ደፋርነትን ተጠቀም፤ ነገር ግን ኃያል ነትህን አትጠቀም፤ እናም ደግሞ በፍቅር ትሞላ ዘንድ ስሜትህን በሙሉ ተቆጣጠር፤ ከስራ ፈትነት ራስህን ቆጥብ።

፲፫ እንደ ዞራማውያን አትፀልይ፣ እነ ርሱ ሰዎች እንዲሰሙአቸው እንደሚፀልዩ እናም ለብልህነታቸው እንዲወደሱ እንደ ሚፈልጉ አይተሃቸዋልና።

፲፬ አምላክ ሆይ እኛ ከወንድሞቻችን ᵐየተሻልን ስለሆንን እናመሰግንሀለን አት በል፤ ነገር ግን ጌታ ሆይ ᵃለከንቱነቴ ይቅር በለኝ፣ እናም ወንድሞቼንም በምህረትህ አስታውስ በል—አዎን፣ በሁሉም ጊዜ በእ ግዚአብሔር ፊት ከንቱነትህን አረጋግጥ።

፲፭ እናም ጌታ ነፍስህን ይባርከና፣ በመ ጨረሻው ቀን በሰላም እንድትቀመጥ በመ ንግስቱ ይቀበልህ። አሁን ልጄ ሂድ፣ እናም ለዚህ ህዝብ ቃሉን አስተምር። ንቃ። ልጄ ደህና ሁን።

አልማ ለልጁ ቆሪያንቶን የሰጠው ትዕዛዛት።

ከምዕራፍ ፴፱ እስከ ፴፪ አጠቃሎ የያዘ።

ምዕራፍ ፴፱

የፍትህወት ኃጢያት እርኩሰት ነው—የቆ ሪያንቶን ኃጢያት ዞራማውያንን ቃሉን ከመቀበል አገዳቸው—የክርስቶስ ቤዛነት በፊት የነበሩትን ታማኞች ለማዳን ወደ ኋላ ተመልሶ የሚሠራ ነው። በ፳፻፱ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንግዲህ ልጄ፣ ለወንድምህ ከተ ናገርኩት የበለጠ ለአንተ በመጠኑ የምናገ ረው አለኝ፤ እነሆ፣ የወንድምህን ፅኑነት፣ ታማኝነት እናም የእግዚአብሔርን ትዕዛ ዛት በመጠበቅ ትጋቱን አልተመለከትህምን? እነሆ፣ ለአንተስ ጥሩ ምሳሌ አልሆነምን?

፪ አንተ ግን ᵐበዞራማውያን ሰዎች መካ ከል ወንድምህ እንዳደረገው ለቃላቴ ጆሮ ህን አልሰጠኸኝም። እንግዲህ ይህ እኔ ከአ ንተ የምቃረንበት ነው፤ አንተም በጉልበትህ እና በጥበብህ እየኮራህ ሄደህ ነበር።

፫ እንግዲህ ልጄ ይህ ብቻም አይደለም። ለእኔ የሚያሳዝነኝን አድርገሃል፤ ምክንያ ቱም አገልግሎቱን ጥለህ ሄደሃል፣ እናም በላማናውያን ምድር ዳርቻም ᵐጋለሞታዋን ኢሳቤልን ተከትለህ ወደ ሲሮን ምድር ሄደ ሃል።

፬ አዎን፣ እርሷም የብዙዎቹን ልብ ᵐሰር ቃለች፤ ነገር ግን ልጄ ይህ ለአንተ የምታ መካኝበት አይሆንም። በአደራ ለተሰጠህም ለአገልግሎቱ ታማኝ መሆን ነበረብህ።

፭ ልጄ ᵐእነዚህ ነገሮች በጌታ አመለካከት የረከሱ እንደሆኑ፤ አዎን፣ የንፁሃንን ደም ከማፍሰስ ወይንም መንፈስ ቅዱስን ከመ ካድ በቀር ከሌሎች ኃጢአቶች ሁሉ ይበ ልጥ አስከፊ መሆናቸውን አታውቅምን?

፮ እነሆም፣ በአንተ ውስጥ ስፍራ የነበረ ውን መንፈስ ቅዱስን ᵐየምትክድ ከሆነ፤ እናም እንደካድከው ካወቅህ፤ እነሆ፣ ይህ ᵃይቅር የማይባል ኃጢያት ነው፤ አዎን፣

፱ *ሀ* ሔሊ. ፭፡፱።
ለ ሞዛያ ፲፮፡፱።
፲፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. ኩራት።
፲፪ *ሀ* አልማ ፴፩፡፲፮።
ለ ሉቃ. ፲፰፡፲–፲፡።
፴፱ ፪ *ሀ* አልማ ፴፰፡፲።
፫ *ሀ* ቅ.መ.መ. ስሜታዊ፣ ስሜታዊነት።
፬ *ሀ* ምሳ. ፯፡፮–፳፯።
፭ *ሀ* ቅ.መ.መ. በወሲብ የስነ ምግባር ጉድለት።
፮ *ሀ* ት. እና ቃ. ፴፮፡፴፭–፴፮።
ለ ቅ.መ.መ. ይቅርታ የሌለው ኃጢያት።

እናም ማንም ከእግዚአብሔር ብርሃንና እውቀት ተቃራኒ በመሆን የገደለ፤ ለእርሱም ፦ይቅርታን ማግኘት ቀላል አይደለም፤ አዎን ልጄ እንዲህ እልሃለሁ፣ ለእንደዚህ ዓይነቱ ሰው ይህን ይቅርታን ማግኘት ቀላል አይደለም።

፯ እናም አሁን ልጄ፣ እንደዚህ አይነት በሆኑ ᵐወንጀሎች ጥፋተኛ እንዳልሆንክ ምኞቴ ነበር። ለአንተ መልካም ባይሆን ኖሮ ነፍስህን ለማሰቃየት ስለወንጀልህ በመናገር አልቀጥልም።

፰ ነገር ግን እነሆ፣ ወንጀልህን ከእግዚአብሔር ለመደበቅ አትችልም፤ እናም ንስሃ ካልገባህ በመጨረሻው ቀን በአንተ ላይ ለምስክርነት ይቆማሉ።

፱ እንግዲህ ልጄ፣ ለኃጢያትህ ንስሃ መግባትና መተው፣ እናም በዓይንህ ᵐምኞት ከእንግዲህ እንዳትጓዝ እፈልጋለሁ፤ ነገር ግን እነዚህን ነገሮች ሁሉ ᶣአስወግድ፤ ይህንን ካላደረግህ በምንም ዓይነት የእግዚአብሔርን መንግስት ልትወርስ አትችልምና። አቤቱ፣ አስታውስ፣ እናም በእራስህ ውሰደው፣ ከእነዚህም ነገሮች ራስህን አስወግድ።

፲ እናም በድርጊቶችህ ከታላላቅ ወንድሞችህ ጋር እንድትመካከር አዝሃለሁ፤ እነሆም አንተ ወጣት ነህና፣ በወንድሞችህ እንክብካቤን ያስፈልግሀል። እናም ምክራቸውን አድምጥ።

፲፩ በከንቱ ወይንም በማይረባ ነገር እንድትመራ አታድርግ፤ በኃጢአተኞች ጋለሞታዎች በድጋሚ ዲያብሎስ ልብህን እንዲያስተው አትፍቀድለት። እነሆ ልጄ ሆይ፣ ᵐበዞራማውያን ላይ እንዴት ያለ ታላቅ ክፋትን አምጥተሃል፤ የአንተን ᶣፀባይ በተመለከቱ ጊዜም ቃሌን አላመኑትምና።

፲፪ እናም አሁን የጌታ መንፈስ እንዲህ ሲል ተናገረኝ፥ የብዙ ሰዎችን ልብ ወደጥፋት እንዳይመሩ ልጆችህን መልካም እንዲያደርጉ ᵐእዘዛቸው፤ ስለዚህ ልጄ፣ እግዚአብሔርን በመፍራት ከጥፋቶችህ እንድትቆጠብ አዝሃለሁ፤

፲፫ በሙሉ አዕምሮህ፣ ኃይልህ፣ እናም ጉልበትህ ወደ ጌታ እንድትመለስ፤ ከእንግዲህ የማንንም ልብ ወደ ክፋት እንዳትመራም፤ ነገር ግን ወደ እነርሱ እንድትመልሳቸው፣ እናም ጥፋትህንና የሰራኸውን ስህተት ᵐእንድትቀበል አዝሀለሁ።

፲፬ ሀብትን እንዲሁም የዚህን ዓለም ከንቱ ነገሮች ᵐአትፈልግ፤ እነሆም፣ ከአንተም ጋር ይዘሀቸው ለመሄድ አትችልም።

፲፭ እናም አሁን ልጄ፣ ስለክርስቶስ መምጣት በመጠኑ እነግርሃለሁ። እነሆ፣ እርሱ ነው በእርግጥ የዓለምን ኃጢያት ሊወስድ የሚመጣው፤ አዎን፣ ለዚህ ህዝብ የደህንነትን የምስራች ዜና ለማወጅ ይመጣል።

፲፮ እናም እንግዲህ ልጄ፣ ለዚህ አገልግሎት የተጠራኸው አዕምሮአቸውን ለማዘጋጀት፣ ወይም ደህንነት ይመጣለት ዘንድ፣ በሚመጣበት ጊዜም ቃሉን እንዲሰሙ ᵐየልጆቻቸውን አዕምሮ እንዲያዘጋጁ ለህዝቡ የምስራቹን ዜና እንድትናገር ነበር።

፲፯ እናም እንግዲህ በዚህ ጉዳይ ጭንቅ ትህን አቀልልሃለሁ። እነሆ፣ እነዚህ ነገሮች አስቀድመው ለምን እንዲታወቁ ተደረጉ ብለህ ትገረማለህ። እነሆ እንዲህ እልሃለሁ፤ በዚህን ጊዜ ያለው ነፍስ በክርስቶስ መምጫ ጊዜ እንደሚኖረው ነፍስ ለእግዚአብሔር ውድ የሆነ አይደለምን?

፲፰ የቤዛነት ዕቅድ ለዚህ ህዝብ እናም ለልጆቻቸው እንዲያውቁት መደረጉ አስፈላጊ አይደለምን?

፲፱ ጌታ መላዕክቱን ለልጆቻችን፣ ወይም እርሱ ከመጣበት ጊዜ በኋላ፣ እነዚህን የም

፯ *ሐ* ት. እና ቃ. ፳፬፡፲። ቅ.መ.መ. ይቅርታ ማድረግ።
፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. በደል።
፱ *ሀ* ቅ.መ.መ. ስጋዊ።
ለ ቮ ኔፊ ፲፪፡ ፴።
፲፩ *ሀ* አልማ ፴፭፡ ፪–፲፡፡
ለ ሮሜ ፪፡ ፳፩–፳፫፣ ፲፡፡ ፲ቮ፣ አልማ ፡፡ ፲፩።
፲፪ *ሀ* ቅ.መ.መ. ማስተማር፣ አስተማሪ፣ የእግዚአብሔር ትእዛዛት።
፲ቮ *ሀ* ሞዛያ ፳፯፡ ፴፡–፴፭።
፲፡ *ሀ* ማቴ. ፮፡ ፳፭–፴፡፡ ያዕቆ. ፪፡ ፲፳–፲፱፣ ት. እና ቃ. ፮፡ ፯–፯፣ ፳፳፡ ፴፩–፴፪።
፲፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. ቤተሰብ—የወላጆች ሀላፊነቶች።

ስራቹን ዜና ያውጅ ዘንድ ለመናገር መላኩ፣ ወደ እኛም ለመላክ የሚቀለው አይደለምን?

ምዕራፍ ፯

ክርስቶስ ለሰው ልጆች ሁሉ ትንሣኤ እን ዲሆን አደረገ—ፃድቃን ሆነው የሞቱት ወደገነት ይሄዳሉ፣ እናም ኃጢአተኛ ሆነው የሞቱት እስከትንሳኤው ቀን ለመጠ በቅ ወደ ድቅድቅ ጨለማ ይሄዳሉ—በት ንሣኤ ሁሉም ነገር ወደ ተገቢው እናም ፍፁም ወደሆነው ቅርፅ ይመለሳል። በ፳፲ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እንግዲህ ልጄ፣ ለአንተ በተጨማሪ የምለው ነገር ይህ ነው፤ ምክንያቱም አዕ ምሮህ ስለሙታን ትንሣኤ ተጨንቋልና።

፪ እነሆ፣ እንዲህ እልሃለሁ፣ ትንሣኤ የለም፣ ወይም በሌላ አነጋገር እንዲህ እላ ለሁ፣ ክርስቶስ ከመምጣቱ [ሀ]በኋላ ድረስ ይህ የሚሞተው [ለ]ወደማይሞተው፣ ይህ የሚበሰብሰው ወደማይበሰብሰው [ሐ]አይለ ወጥም።

፫ እነሆ፣ እርሱ የሙታን ትንሣኤ እን ዲሆን ያደርጋል። ነገር ግን እነሆ፣ ልጄ፣ [ሀ]ትንሳኤው ገና ነው። እንግዲህ፣ ሚስጥሩን እገልፅልሃለሁ፤ ይሁን እንጂ፣ እግዚአብ ሔር እራሱ ካልሆነ በቀር ማንም የማያውቃ ቸው ብዙ በአምላክ [ለ]የተደበቁ [ሐ]ሚስጥሮች አሉ። ነገር ግን እግዚአብሔርን አውቀው ዘንድ በትጋት የጠየቅሁትን አንድ ነገር ለአ ንተ አሳይሃለሁ፤ እርሱም ትንሣኤን በተ መለከተ ነው።

፬ እነሆ፣ ሁሉም ከሙታን እንዲነሱበት የተወሰነ ጊዜ አለ። እንግዲህ ይህ [ሀ]የምመ ጣበትን ጊዜ ማንም አያውቅም፤ ነገር ግን የተወሰነውን ጊዜ እግዚአብሔር ያውቃል።

፭ እንግዲህ የመጀመሪያዎቹም ሆኑ [ሀ]ሁለ ተኛዎቹ፣ እንዲሁም ሦስተኞቹ ከሞት የሚነሱበት ጊዜ መኖሩ ልዩነት የለውም፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር እነዚህን ነገ ሮች ሁሉ [ለ]ያውቃልና፤ እናም ይህ እንደ ሚሆን—ሁሉም ከሞት የሚነሱበት የተወ ሰነ ጊዜ እንዳለ ማወቅ ለእኔ ይበቃኛል።

፮ እንግዲህ በሞት እናም በትንሳኤ መካ ከል ጊዜ መኖሩ አስፈላጊ ነው።

፯ እናም እንግዲህ እንዲህ ብዬ እጠይቃ ለሁ፥ የሰው [ሀ]ነፍስ ከሞተበት ጊዜ ጀምሮ ለትንሣኤው እስከተወሰነበት ጊዜ ድረስ ምን ይሆናል?

፰ እንግዲህ ሰዎች እንዲነሱ የተወሰነ ላቸው ጊዜ ከአንዴ የበለጠ ቢሆን ምንም ልዩነት አያመጣም፤ ምክንያቱም ሁሉም በአንዴ አይሞቱምና፣ እናም ይህም ምንም አይደለም፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ሁሉም እንደ አንድ ቀን ነው፤ እናም ጊዜ በሰዎች ብቻ ይለካል።

፱ ስለዚህ፣ ሰዎች ከሞት የሚነሱበት ቀን ተወስኗል፤ እናም በሞትና በትንሣኤ መካ ከል ጊዜ አለ። እናም እንግዲህ፣ ይህን ጊዜ በተመለከተም፣ የሰዎች ነፍስ ምን ይሆናል ብዬ ጌታን በትጋት የጠየቅሁት ይህን ነገር ነው፤ እናም የማውቀው ነገር ይህን ነው።

፲ እናም ሁሉም ከሞት የሚነሱበት ጊዜው ሲደርስ፤ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የተ ወሰነውን [ሀ]ጊዜ በሙሉ ማወቁንም ያው ቃሉ።

፲፩ እንግዲህ፣ [ሀ]በሞትና በትንሣኤ መካ ከል የነፍስ ሁኔታን በተመለከተ—እነሆ፣ የሰዎች መንፈስ ሁሉ ከዚህ ሟች ከሆነው ሰውነታቸው እንደተለየ፣ አዎን፣ የሰዎች መንፈስ ሁሉ፣ መልካምም ይሁኑ መጥፎ፣ ህይወትን ወደ ሰጣቸው ወደ እግዚአብሔር

፯ ፪ *ሀ* ፩ ቆሮ. ፲፭፡፳፡ ፳።
ለ ሞዛያ ፲፮፡፲–፲፫። ቅ.መ.መ. የማይሞት፣ አለሟችነት።
ሐ ፩ ቆሮ. ፲፭፡፶፫–፶፬።
፫ *ሀ* ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
ለ ት. እና ቃ. ፳፭፡፩፣ ፲፯፡፭፣ ፻፳፩፡ ፻፴፩።
ሐ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ሚስጥሮች።
፩ *ሀ* ዮሐ. ፭፡ ፳፰–፳፱።
፭ *ሀ* ሞዛያ ፳፮፡ ፳፱–፳፭፣ ት. እና ቃ. ፻፫፡ ፲፳፡ ፫፯፡ ፻፲፭።
ለ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ።
፯ *ሀ* አልማ ፯፡ ፳፭፣ ት. እና ቃ. ፻፴፯። ቅ.መ.መ. ነፍስ።
፲ *ሀ* የሐዋ. ፲፯፡ ፳፭።
፲፩ *ሀ* ሉቃ. ፲፮፡ ፲፭–፳፭፣ ፩ ጴጥ. ፫፡ ፲፰–፲፱፣ ፬፡ ፮፣ ት. እና ቃ. ፫፯፡ ፫፩–፫፪፣ ፻፴፯።

ᵃእንደሚወሰድ በመልአኩ አማካኝነት እን ዳውቀው ተደረገ።

፲፪ እናም እንዲህ ሆነ የፃድቃኖች መን ፈስ፣ ከሁሉም ችግር፣ ውጣ ውረድና ሀዘን ወደሚያርፉበት፣ ᵇገነት ተብላ ወደምት ጠራው፣ ᶜየእረፍት ቦታ፣ ᵈየሰላም ቦታ ውስጥ ወደ ᵉመደስታ ሁኔታ ይገባሉ።

፲፫ እናም እንዲህ ሆነ የኃጢአተኞች መን ፈስ፣ አዎን፣ ክፉዎች የሆኑትም—እነ ሆም፣ የጌታ መንፈስ ፈንታም ሆነ ድርሻ የላቸውም፤ እነሆም፣ ከመልካሙ ስራ ይልቅ መጥፎውን መርጠዋልና፤ ስለዚህ የዲያብሎስ መንፈስ በውስጣቸው ገብ ቷል፣ ቤታቸውንም የእርሱ አድርጎታል—እናም እነኚህ ወደ ᵇድቅድቅ ጨለማ ይጣ ላሉ፤ በዚያም ᶜልቅሶና ዋይታ እናም የጥርስ ማፏጨት ይኖራል፣ ይህም በክፋታቸው የተነሳ፣ በዲያብሎስ ፈቃድም በምርኮ ስለ ተመሩ ይሆናል።

፲፬ እንግዲህ ይህ ᵇየክፉዎች የነፍሳቸው ሁኔታ ነው፤ አዎን፣ በጨለማ ውስጥ እናም በእራሳቸው ላይ የእግዚአብሔር ሀይለኛ ንዴት ቁጣ በመጠበቅ አሰቃቂውና ᶜበአስ ፈሪውም በሆነ በእንደዚህም አይነት ሁኔታ ሲቆዩ፣ ፃድቃኖችም እስከትንሳኤው ድረስ በገነት ይቆያሉ።

፲፭ እንግዲህ፣ ከትንሳኤው በፊት እንደ ዚህ ዓይነቱን የነፍስ ደስታን እና መከራን የመጀመሪያው ትንሳኤ ነው በማለት የሚ ረዱት ጥቂት ሰዎች አሉ። አዎን፣ በተነገ ሩት ቃላት መሠረት የነፍስ ወይንም የመ ንፈስ መነሳትንና በደስታ ወይንም በችግር መሰየም ምናልባት ትንሳኤ ተብሎ ሊጠራ እንደሚችል እቀበለዋለሁ።

፲፮ እናም እነሆ፣ በድጋሚ በክርስቶስ ከሙታን መነሳት ድረስ የነበሩት፣ ወይንም ያሉት ወይንም የሚኖሩት ሁሉ ትንሣኤ፣ ᵇየፊተኛው ᶜትንሳኤ እንዳለም ተነግሯል።

፲፯ አሁን፣ በዚህ ሁኔታ የተነገረው ይህ የመጀመሪያው ትንሳኤ፣ የነፍስ ትንሳኤ እንዲሁም የደስታቸው ወይም የሥቃያ ቸው ᵇስያሜ ሊሆን እንደሚችል አልገመ ትንም። ይህ ትርጉሙ ይሆናል ብለህ መገ መትም አትችልም።

፲፰ እነሆ፣ እንዲህ እልሃለሁ፣ አይደ ለም፤ ነገር ግን ይህ ከአዳም ጀምሮ እስከ ᵇክርስቶስ ትንሣኤ ድረስ ለነበሩት የነፍስ እና የስጋ ውህደት ማለት ነው።

፲፱ እንግዲህ ቀድሞ የተነናግርኩባቸው ኃጥአንም ሆነ ፃድቃን ነፍሳቸው ከስጋቸው ጋር በአንድ ጊዜ ይዋሃዳል ብዬ አልናገርም፤ ሁሉም ይነሳሉ ማለቴ ብቻ በቂ ነው፤ ወይም በሌላ አነጋገር፣ ትንሣኤአቸው ከክርስቶስ ትንሳኤ በኋላ ከሞቱት ᵇበፊት ይሆናል።

፳ እንግዲህ፣ ልጄ፣ ትንሣኤያቸው በክ ርስቶስ ትንሣኤ ይመጣል አላልኩሁም፤ ነገር ግን እነሆ፣ በክርስቶስ ትንሣኤ እን ዲሁም ወደ ሰማይ ᵇባረገበት ጊዜ የፃድቃ ኖች ነፍስ ከስጋቸው ጋር መዋሃዱን አስተ ያየቴን እሰጣለሁ።

፳፩ ነገር ግን በትንሣኤውም ሆነ ከት ንሣኤውም በኋላ እንደዚህ አልልም፤ ነገር ግን ይህንን ያህል እናገራለሁ፣ ሙታን እን ደሚነሱ፣ ነፍስም ከስጋ ዳግም እስከሚገ ናኝ እንዲሁም በእግዚአብሔር በተወሰነ ላቸው ቀን እንደስራቸው በእግዚአብሔር ፊት ᵇበመቆም እስከሚፈረድባቸው ድረስ በሞትና በአካል ትንሳኤ መካከል ᶜጊዜ፣ እናም ነፍስ ᵈበደስታ ወይም ᵉበስቃይ የሚ ገኝበት ጊዜ አለ።

፲፩ ለ መክ. ፲፪፡፯፣
፪ ኔፊ ፱፡ ፴፰።
፲፪ ሀ ቅ.መ.መ. ገነት።
ለ ቅ.መ.መ. እረፍት።
ሐ ት. እና ቃ. ፵፭፡ ፵፯።
ቅ.መ.መ. ሰላም።
መ ቅ.መ.መ. ደስታ።
፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. ሲያል።
ለ ማቴ. ፰፡ ፲፪፣
ሞዛያ ፲፯፡ ፪።
፲፬ ሀ ት. እና ቃ. ፲፴፰፡ ፳።
ለ ያዕቆ. ፮፡ ፲፫፣
አልማ ፴፪፡ ፴፬፣
ሙሴ ፯፡ ፩።
፲፮ ሀ ያዕቆ. ፪፡ ፲፩፣
ሞዛያ ፲፭፡ ፳፩–፳፫።
ለ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
፲፯ ሀ ት. እና ቃ. ሮሜ፡ ፲፣ ፴፪፣
፶–፶፩።
፲፰ ሀ ማቴ. ፳፯፡ ፶፪–፶፫።
፲፱ ሀ ሞዛያ ፲፭፡ ፳፯።
፳ ሀ ቅ.መ.መ. ወደ ሰማይ ማረግ።
፳፩ ሀ አልማ ፵፪፡ ፳፫።
ለ ሉቃ. ፳፫፡ ፴፱–፵፫።
ሐ ቅ.መ.መ. ገነት።
መ ቅ.መ.መ. ሲያል።

፰፪ አዎን፣ ይህም በነቢያት አንደበት የተ ነገሩትን ነገሮች በሙሉ ዳግሞ መመለስን ይመጣል።

፰፫ [ሀ]ነፍስ ወደ [ለ]ስጋ፣ ስጋም ወደ ነፍስ [ሐ]በዳግም ይመለሳል፤ አዎን፣ እናም ማንኛ ውም እጅና እግር እንዲሁም መገጣጠሚያ ወደ ቀድሞ ቦታው ይመለሳል፤ አዎን፣ የራስ ፀጉርም ቢሆን አይጠፋም፤ ነገር ግን ሁሉም ነገር ወደ ተገቢው እናም ትክክለኛ አቋሙ ይመለሳል።

፰፬ እናም እንግዲህ፣ ልጄ፣ ይህ በነቢያት አንደበት [ሀ]የተነገረው ዳግሞ መመለስ ነው—

፰፭ እና ከእዚያም ፃድቃኖች በእግዚአ ብሔር መንግስት ያበራሉ።

፰፮ ነገር ግን እነሆ፣ አሰቃቂው [ሀ]ሞት በኃጢአተኞች ላይ ይሆናል፤ ፅድቅ ለሆ ኑት ነገሮች ሞተዋልና፤ ምክንያቱም እነ ርሱ ንፁህ አይደሉምና፣ እናም ምንም [ለ]እርኩስ ነገር የእግዚአብሔርን መንግስት ሊወርስ አይችልም፤ ነገር ግን መጥፎ የሆ ኑትን የስራቸውን ውጤት እንዲካፈሉ ይጣ ላሉ፣ እናም መራራውን አተላ ይጎነጫሉ።

ምዕራፍ ፶፩

በትንሣኤ ሰዎች መጨረሻ ለሌለው ደስታ ወይንም መጨረሻ ለሌለው ስቃይ ይመ ጣሉ—ኃጢያት በጭራሽ ደስታ ሆኖ አያ ውቅም—ስጋ ለባሽ ሰዎች በዓለም ሳሉ ከእግዚአብሔር ጋር አይደሉም—ማንኛ ውም ሰው በትንሣኤው ወቅት፣ ሟች በነ በረበት ጊዜ ያገኘውን ባህሪና ፀባይ እንደ ገና ይቀበላል። በ፳፬ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንግዲህ ልጄ፣ ስለተነገሩት ዳግሞ መመለስ በተመለከተ በመጠኑ የም ለው አለኝ፤ እነሆም፣ አንዳንድ ሰዎች የቅ ዱሳን መፃህፍትን ትርጉም [ሀ]ያጣምማሉ፣ እናም በዚህ ነገር ምክንያት እጅግ [ለ]ተሳስ ተዋል። እናም አዕምሮህ ይህንን ነገር በተ መለከተ ደግሞም እንደተጨነቀ አስተውላ ለሁ። ነገር ግን እነሆ፣ ላንተ እገልፅልሃለሁ።

፪ ልጄ እንዲህ እልሃለሁ፣ የዳግሞ መመ ለስ ዕቅድ በእግዚአብሔር ፍትህ መሰረት አስፈላጊ ነው፤ ምክንያቱም ሁሉም ነገ ሮች ወደ ተገቢው ስርዓት እንዲመለሱ አስ ፈላጊ ነው። እነሆ፣ በክርስቶስ ኃይል እና ትንሣኤ መሰረት የሰው ነፍስ ወደ ሰውነቱ መመለሱ፣ እናም ማንኛውም [ሀ]የሰውነት ክፍል ወደ ቀድሞው መመለሱ አስፈላጊና ፍትህ ነው።

፫ እናም [ሀ]በእግዚአብሔር ፍርድ ሰዎች እንደስራቸው [ለ]እንዲፈረድባቸው አስፈ ላጊ ነው፤ እናም በዚህ ህይወት [ሐ]ስራቸው መልካም ከሆነና፣ የልባቸው ፍላጎት መል ካም ከሆነ፣ በመጨረሻው ቀን ደግሞ መል ካም ወደሆነው [መ]መመለስ አለባቸው።

፬ እናም ስራቸው መጥፎ ከሆነ፣ በእነርሱ ላይ ለመጥፎ [ሀ]ይመለሱባቸዋል። ስለዚህ፣ ሁሉም ነገር ወደ ተገቢው ስርዓት ይመለ ሳል፣ ማንኛውም ነገር ወደ ተፈጥሮአዊው አቋም ይመለሳል—[ለ]ሟች የሆነው የማይ ሞት በመሆን፣ [ሐ]የሚበሰብሰው ወደ ማይ በሰብሰው—የእግዚአብሔርን መንግስት ለመውረስ [መ]መጨረሻ ወደሌለው ደስ ታም ይነሳሉ—አለበለዚያም የዲያብሎስን መንግስት ለመውረስ መጨረሻ ወደሌለው ስቃይ ይነሳሉ፣ አንዱ በዚህኛውም፣ ሌላው በሌላኛው—

፰፫ [ሀ] ይህም መንፈስ ማለት ነው።
ት. እና ቃ. ፹፰፡፲፭–፲፯።
ቅ.መ.መ. ነፍስ።
[ለ] ቅ.መ.መ. ሰውነት።
[ሐ] ፪ ኔፊ ፱፡ ፲፪–፲፫፣
አልማ ፲፩፡ ፶–፶፭።

፰፬ [ሀ] ኢሳ. ፳፭፡ ፲፱።

፰፭ [ሀ] ፩ ኔፊ ፲፭፡ ፴፫፣
አልማ ፲፪፡ ፲፯።
[ለ] አልማ ፲፩፡ ፴፯።

፶፩ ፩ [ሀ] ፪ ጴጥ. ፩፡ ፳፣ ፫፡ ፲፯፣
አልማ ፲፫፡ ፳።
[ለ] ቅ.መ.መ. ክህደት።

፪ [ሀ] አልማ ፶፡ ፳፫።

፫ [ሀ] ቅ.መ.መ. ፍትህ።
[ለ] ቅ.መ.መ. መልስ
መስጠት፣ ሂሳብ፣
ተጠያቂነት፣ ሀላፊነት፣
ዳኛ፣ ፍርድ።
[ሐ] ቅ.መ.መ. ስራዎች።
[መ] ሐሌ. ፲፬፡ ፴፩።

፬ [ሀ] አልማ ፶፪፡ ፳፰።
[ለ] ፪ ኔፊ ፱፡ ፲፪–፲፫፣
ት. እና ቃ. ፹፭፡ ፲ ፲፯።
ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
[ሐ] ፩ ቆሮ. ፲፭፡ ፶፩–፶፭።
[መ] ቅ.መ.መ. የዘለዓለም
ህይወት።

፭ አንደኛው ደስታን በመፈለግ ለደ
ስታ ይነሳል፣ ወይም ለመልካም ፍላጎ
ቱም መልካም ሆኖ ይነሳል፣ እናም ለመ
ጥፎ ፍላጎቱ ሌለኛው መጥፎ ሆኖ ይነሳል፤
ቀኑን በሙሉ ክፉ ማድረግ በመፈለጉ ጨለ
ማው በሚመጣበት ጊዜ ለክፋቱ ብድራቱን
ይቀበላል።

፮ እናም በሌላ መልኩም እንዲሁ ነው።
ለኃጢአቱ ንስሃን ከገባ፣ እናም እስከ ዘመኑ
ፍፃሜም ድረስ ፅድቅን ከፈለገ እንዲህ በማ
ድረጉ የጽድቅን ዋጋ ይቀበላል።

፯ በጌታ የሚድኑት ᵐእነኚህ ናቸውና፤
አዎን፣ እነዚህ መጨረሻ ከሌለው የጨለ
ማው ምሽት የወጡት፣ የተለቀቁት ናቸው፤
እናም እንደዚህም ይጸናሉ ወይም ይወድ
ቃሉ፤ እነሆም፣ መልካምም ይሁን መጥፎ
ለማድረግ በራሳቸው ላይ ᵃፈራጅ ይሆናሉ።

፰ እንግዲህ፣ የእግዚአብሔር አዋጅ
ᵐየሚለወጡ አይደሉም፤ ስለዚህ፣ በጌታ
መንገድ ለሚራመደው መንገዱ ተዘጋጅ
ቷል፣ በዚህ የሚራመድም ይድናል።

፱ እናም አሁን እነሆ ልጄ፣ ከዚህ ጊዜ
በፊት ኃጢያትን በመፈፀም እንዳደረ
ከው፣ በእነዚህ ትምህርቶች በተመለከተ
በአምላክህ ላይ ᵐአንድም እንኳን በደልን
አታድርግ።

፲ ስለዳግሞ መመለስ በመነገሩ ከኃጢ
ያት ወደ ደስታ እመለሳለሁ ብለህ አትገ
ምት። እነሆ እንዲህ እልሃለሁ ᵐክፋት በፍ
ፁም ደስታ ሆኖ አያውቅም።

፲፩ እናም አሁን ልጄ፣ ᵐበተፈጥሮአዊው
ሁኔታ ያሉ ሰዎች በሙሉ፣ ወይንም እኔ
እንደምለው ᵃበስጋ ያሉት ሁሉ፣ በመራራ
መርዝና፣ በክፋት ሰንሠለት ናቸው፤ በዓ
ለም ᵃያለ አምላክ ናቸው፣ እናም ከእግ
ዚአብሔር ባህርይ ጋር ተቃርነዋል፤ ስለ
ዚህ፣ ከደስታ ባህርይ ጋርም ተቃራኒ በሚ
ሆን ሁኔታ ውስጥ ናቸው።

፲፪ እናም አሁን እነሆ፣ ዳግሞ መመለስ
የሚለው ቃል ትርጉሙ ነገር ከተፈጥሮ
አዊው ሁኔታ ወስዶ እናም ተፈጥሮአዊ
ወዳልሆነ ቦታ ማስቀመጥ፣ ወይንም ከተ
ፈጥሮአዊው ተቃራኒ የሆነውን ቦታ ማስ
ቀመጥ ነውን?

፲፫ ልጄ ሆይ፣ ሁኔታው ይህ አይደለም፣
ነገር ግን የዳግሞ መመለስ የቃል ትርጉም
መጥፎን ለመጥፎ፣ ስጋን ለስጋ ወይንም
ዲያብሎስን ለዲያብሎስ መልሶ ማምጣት
ነው—መልካም ለሆነው መልካምን፣ ፃድቅ
ለሆነው ፅድቅን፤ ፍትሃዊ ለሆነው ፍትህን፤
መሃሪ ለሆነው ምህረትን ማምጣት ነው።

፲፬ ስለዚህ ልጄ፣ ለወንድሞችህ መሃሪ
ለመሆንህ እርግጠኛ ሁን፣ ለሰዎች ᵐፍትሃዊ
ሁን፣ በትክክል ᵃፍረድ፣ እናም ያለማቋ
ረጥ ᵐመልካምን ስራ፤ እናም ይህንን
ሁሉ የምታደርግ ከሆነ ደመወዝህን ታገ
ኛለህ፤ አዎን፣ ᵐምህረት በድጋሚ ይመ
ለስልሃል፤ በድጋሚም ፍትህ ይመለስል
ሃል፣ በድጋሚም ጻድቃዊ ፍርድ ይመለ
ስልሃል፣ እናም በድጋሚ መልካም ደመ
ወዝ ታገኛለህ።

፲፭ የምትልከው በድጋሚ ወዳንተው
ይመጣል፣ እናም ዳግሞ ይመለሳልና፤ ስለ
ዚህ ዳግሞ መመለስ የሚባለው ቃል ኃጢ
አተኛውን ሙሉ በሙሉ ይፈርድበታልም፣
በምንም ዓይነት አያፀድቀውም።

ምዕራፍ ፵፪

*ሟችነት ሰዎችን ንስሃ እንዲገቡ እናም
እግዚአብሔርን እንዲያገለግሉ የሚያስ
ችል የሙከራ ጊዜ ነው—የአዳም መውደቅ*

፲ ሀ ት. እና ቃ. ፫፲፮፡ ፱–፫።
ለ ፪ ኔፊ ፪፡ ፳፯፤
አልማ ፵፪፡ ፳፯፤
ሔለ. ፲፬፡ ፴።
ቅ.መ.መ. ነጻ ምርጫ።
፲፩ ሀ ት. እና ቃ. ፭፡ ፴፯።
፲፪ ሀ ት. እና ቃ. ፵፪፡ ፳፫–፳፯።
፲ ሀ መዝ. ፴፪፡ ፲፣
ኢሳ. ፶፯፡ ፳–፳፩፤
ሔለ. ፲፫፡ ፴፯።
፲፩ ሀ ሞዛያ ፫፡ ፲፱።
ቅ.መ.መ. ፍጥረታዊ ሰው።
ለ ቅ.መ.መ. ስጋዊ።
ሐ ኤፌ. ፪፡ ፲፪።
፲፬ ሀ ቅ.መ.መ. ታማኝ፣
ታማኝነት።
ለ ዮሐ. ፲፡ ፳፬፤
ት. እና ቃ. ፲፩፡ ፲፪።
ሐ ት. እና ቃ. ፮፡ ፲፫፣
፶፯፡ ፳፯–፳፯።
መ ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።

በሰው ዘር ሁሉ ላይ ጊዜያዊ እናም መንፈ ሳዊ ሞትን አመጣ—ቤዛነት በንስሃ አማ ካይነት ይመጣል—እግዚአብሔር እራሱ ለዓለም ኃጢያት ክፍያን ይከፍላል—ንሰሃ የሚገቡ ምህረትን ያገኛሉ—ሌሎች በሙሉ በእግዚአብሔር ፍትህ ስር ናቸው—ምህ ረት በኃጢያት ክፍያው አማካኝነት ይመ ጣል—እውነተኛ ንሰሃ ገቢዎች ብቻ ይድ ናሉ። በ፳፩ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንግዲህ ልጄ፣ ኃጢአተኞችን በመቅጣት [a]የእግዚአብሔርን ፍትህ በተ መለከተ፣ አንተ መረዳት የማትችለው አዕ ምሮህን የሚረብሽ ከዚህ የበለጠ በመጠኑ እንዳለ አስተውላለሁ፤ ኃጢአተኞች ወደ [b]ሥቃይ መመደባቸው ፍትሃዊ አይደለም በማለት ገምተሃልና።

፪ እንግዲህ እነሆ ልጄ ይህንን ነገር ለአ ንተ እገልፅልሃለሁ። እነሆም፣ ጌታ እግ ዚአብሔር የመጀመሪያ ቤተሰቦቻችንን ከተወሰዱበት ስፍራ መሬቱን እንዲያ ርሱ ከዔድን ገነት [c]ካስወጣቸው በኋላ—አዎን፣ ሰውን አስወጣ፣ እናም ጌታ እግ ዚአብሔር [d]በዔድን ገነት በስተምስራቅ ጫፍ፣ [e]ኪሩቤልን፣ እናም የምትገለባበጥ የነበልባል ሰይፍን፣ [f]የህይወት ዛፍን ለመ ጠበቅ አስቀመጠ—

፫ እንግዲህ፣ ሰው መልካሙንና መጥፎ ውን በማወቅ እንደ አምላክ መሆኑን እና ያለን፤ እናም እጁን በመዘርጋትና፣ ደግሞ ከህይወት ዛፍ በመውሰድ፣ እናም በመብ ላት ለዘለዓለም ለመኖር የሚችል እንዳይ ሆን፣ ፍሬውንም እንዳይካፈል፣ ጌታ እግ ዚአብሔር ኪሩቤልንና ነበልባል ሰይፉን አስቀመጠ—

፬ እናም ለሰዎች የንስሃ ጊዜ እንደተሰጠም እንመለከታለን፤ አዎን፣ [g]የሙከራ ጊዜ፣ የንስሃ ጊዜና እግዚአብሔርን የሚያገለግ ሉበት ጊዜ ተሰጥቷል።

፭ እነሆም፣ አዳም እጁን በፍጥነት ቢዘ ረጋና ከህይወት ዛፍ ቢበላ፣ እርሱም እንደ እግዚአብሔር ቃልም መሠረት ለዘለአለም በኖረ፣ ለንስሃም ጊዜ ባልኖረው ነበር፣ አዎን፣ እናም ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል ባልተፈፀመና ታላቁ የደህንነት ዕቅድም በከሸፈ ነበር።

፮ ነገር ግን እነሆ፣ ሰዎች [h]እንዲሞቱ ተወስኗል—ስለዚህ ከህይወት ዛፍ እንደ ተለዩም ከምድር ገፅም እንዲሁ ይለያሉ—እናም ሰው ለዘለአለም የጠፋ ሆነ፤ አዎን [i]የወደቀ ሆነ።

፯ እናም እንግዲህ፣ አንተም በዚህ የመ ጀመሪያ ወላጆቻችን ከጌታ ፊት ለጊዜውም ይሁን በመንፈስ [j]መለየታቸውን ትመለከ ታለህ፤ እናም በራሳቸው [k]ፈቃድም ስር የነ በሩ መሆናቸውንም ተመልክተሃል።

፰ እንግዲህ እነሆ፣ ሰው ከዚህ ጊዜያዊ ሞት ደግሞ መዳኑ ትክክለኛ አልነበረም፣ ምክንያቱም ይህ ታላቁን [l]የደስታ ዕቅድ ያጠፋዋልና።

፱ ስለዚህ፣ ነፍስ በጭራሽ ልትሞት ስለማ ትችል፣ እናም የአዳም [m]ውድቀት በሰው ዘር ላይ ሁሉ ከጌታ ፊት እንዲለዩ ጊዜያዊውን ሞት፣ እናም መንፈሳዊውን ሞት በእነርሱ ላይ በማምጣቱ፣ የሰው ዘርም ከዚህ መን ፈሳዊ ሞት ደግሞ ማዳኑ አስፈላጊ ነበር።

፲ ስለዚህ፣ እነርሱ [n]በተፈጥሮአቸው [o]ስጋዊ፣ ስሜታዊ፣ እናም ዲያብሎሳዊ በመሆናቸው፣ ይህ [p]የሙከራ ጊዜ ለእነ ርሱ የዝግጅት ጊዜ ሆነ፤ እርሱም የመዘ ጋጃ ወቅት ሆነ።

፲፩ እናም አሁን ልጄ፣ ይህ የቤዛነት ዕቅድ

---

[a] ፵፪ ፩ ሀ ፪ ኔፊ ፳፯፡፲፣ ሞዛያ ፲፫፡ ፳፯–፳፯። ቅ.መ.መ. ፍትህ።
[b] ፪ ሀ ዘፍጥ. ፫፡ ፳፫–፳፬፣ ሙሴ ፬፡ ፳፰–፴፩። ለ ቅ.መ.መ. ዓድን። ሐ ቅ.መ.መ. ኪሩቤል። መ ዘፍጥ. ፪፡ ፱።
[c] ፪ ሀ አልማ ፴፪፡ ፴፪–፴፫። [d] ፯ ሀ ቅ.መ.መ. ስጋዊ ሞት። ለ ሞዛያ ፲፯፡ ፫–፭። ቅ.መ.መ. የአዳም እና የሔዋን ውድቀት።
[e] ፯ ሀ ፪ ኔፊ ፪፡ ፭፣ ፱፡ ፯፣ ሔለ. ፲፬፡ ፲፯። ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ሞት።
ለ ቅ.መ.መ. ነጻ ምርጫ።
[f] ፴ ሀ አልማ ፴፪፡ ፱፣ ሙሴ ፮፡ ፳፪።
[g] ፱ ሀ ቅ.መ.መ. የአዳም እና የሔዋን ውድቀት።
[h] ፲ ሀ ቅ.መ.መ. ፍጥረታዊ ሰው። ለ ቅ.መ.መ. ስጋዊ። ሐ ቅ.መ.መ. ስጋዊ፣ የሚሞት።

ባይሆን ኖሮ፣ (እንዳልሆነ ቢገመት) እንደ ሞቱ ነፍሳቸው ከጌታ ፊት ስለምትለይ ᵐአሰቃቂ ሁኔታ ላይ እንደምትሆን አስታውስ።

፲፪ እናም እንግዲህ፣ ሰውም ባለመታዘዙ ምክንያት በራሱ ላይ ካመጣው ከወደቀበት ሁኔታ ደግሞ ለመመለስ ምንም መንገድ አልነበረም፤

፲፫ ስለዚህ፣ በፍትህ መሰረት፣ በዚህ በሙከራው ጊዜ፣ አዎን፣ በዝግጅቱ ወቅት፣ ሰዎች ᵐንስሃ ካልገቡ በቀር ᵃየቤዛ ነት ዕቅድ ተግባራዊ ሊሆን አይችልም፤ በዚህ ሁኔታ ካልሆነ በቀር፣ ምህረት የፍት ህን ስራ ካላጠፋው በቀር በስራ ላይ ሊውል አይችልም። እናም የፍትህ ስራ ሊጠፋ አይ ችልም፤ ከጠፋ ግን እግዚአብሔር አምላክ መሆኑን ᵃያቆማል።

፲፬ እናም የሰው ዘር በሙሉ ᵐየወደቁ እን ደነበሩና፣ ᵃበፍትህ እጅ ላይ፣ አዎን እነር ሱን ለዘለአለም ከፊቱ ለመለየት በሚመድ በው የእግዚአብሔር ፍትህ ላይም እንደነ በሩ እንመለከታለን።

፲፭ እናም እንግዲህ፣ የምህረት ዕቅድ የኃ ጢያት ክፍያው ካልተከፈለ በቀር ሊመጣ አይችልም፤ ስለዚህ፣ ᵐየምህረትን ዕቅድ ለመፈፀም፣ ᵃየፍትህን ፍላጎት ለማርካት፣ እግዚአብሔርም ደግሞ ᵃፍፁም፣ እውነ ተኛ አምላክ፣ እናም መሃሪ አምላክ ይሆን ዘንድ፣ እግዚአብሔር እራሱ ለዓለም ኃጥ ያቶች ᵐየኃጢያት ክፍያ ይሆናልና።

፲፮ እንግዲህ፣ የተመደበ ቅጣት ከተመ ደበው የደስታ አላማ ጋር ተቃራኒ የሆነ፣ እንደ ነፍስ ህይወት ᵐዘለአለማዊ የነበረው ቅጣት ከሌለ በስተቀር ለሰዎች ንስሃ ሊመጣ አይችልም፤ የደስታ አላማም እንደ ነፍስ ህይወት ዘለዓለማዊ ነበር።

፲፯ እንግዲህ፣ ሰው ᵐኃጢያትን ካልፈ ፀመ በቀር እንዴት ንስሃ መግባት ይችላል? ᵃህግ ከሌለስ እንዴት ኃጢያትን ሊያደርግ ይችላል? ህግስ ቅጣት ከሌለ በቀር እንዴት ሊኖር ይችላል?

፲፰ እንግዲህ፣ ለሰዎች ᵐየህሊና ፀፀትን ለማምጣት የተመደበ ቅጣት፣ እናም ትክ ክለኛ ህግም ነበር።

፲፱ እንግዲህ፣ ህግ ባይሰጥ ኖሮ—ሰው ᵐከገደለ መሞት ነበረበት—ከገደለ መሞ ትን የሚፈራ ይሆናልን?

፳ እናም ደግሞ፣ ኃጢያትን የሚቃረን ህግም ባይሰጥ ኖሮ ሰዎች ኃጢያትን ለመ ፈፀም አይፈሩም ነበር።

፳፩ እናም ᵐህግ ካልተሰጠ፣ ሰዎች ኃጢ ያትን ቢፈፅሙ፣ ፍትህ ወይም ምህረት ምን ማድረግ ይችሉበታል፣ በፍጥረት ላይ ምንም ጥያቄ አይኖራቸውምን?

፳፪ ነገር ግን ህጉ ተሰጥቷል፣ ቅጣቱም ተመድቧል፣ እናም ᵐንስሃ ተፈቅዷል፤ ይህን ንስሃ መግባትን ምህረትን ትቀበላ ለች፤ አለበለዚያም ፍትህ ፍጡራንን ተጠ ያቂ ያደርጋልና ህግን ያስፈፅማል፣ እናም ህጉ ቅጣትን ያከናውናል፤ ባይሆን ኖሮ ግን የፍትህ ስራ ይጠፋ ነበር፣ እግዚአብሔርም አምላክ መሆኑን ባቆመ ነበር።

፳፫ ነገር ግን እግዚአብሔር አምላክ መሆ ኑን አያቆምም፣ እናም ᵐምህረት ንስሃ በሚ ገቡት ላይ ይሆናል፣ ምህረትም ᵃበኃጢ ያት ክፍያው አማካኝነት ይመጣል፤ የኃ ጢያት ክፍያም የሙታን ᵃትንሳኤን ያመ

፲፩ ሀ ፪ ኔፊ ፱፡ ፯–፱።
፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣ ንስሀ መግባት።
ለ ቅ.መ.መ. የቤዛነት ዕቅድ።
ሐ ፪ ኔፊ ፪፡ ፲፫–፲፭።
፲፭ ሀ አልማ ፳፪፡ ፲፫–፲፭።
ለ ፪ ኔፊ ፪፡ ፭።
፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።
ለ ቅ.መ.መ. ፍትህ።
ሐ ፫ ኔፊ ፲፪፡ ፵፯።
መ ፪ ኔፊ ፱፡ ፯–፲፣ ሞዛያ ፲፯፡ ፯–፳።
ቅ.መ.መ. የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ።
፲፯ ሀ ት. እና ቃ. ፲፱፡ ፲–፲፪።
፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. ኃጢያት።
ለ ሮሜ ፭፡ ፲፭።
፲፰ ሀ ቅ.መ.መ. ህሊና።
፲፱ ሀ ቅ.መ.መ. ግድያ።
፳፩ ሀ ፪ ኔፊ ፱፡ ፳፭–፳፯፣ ሞዛያ ፫፡ ፲፭።
፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣ ንስሀ መግባት።
፳፫ ሀ ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።
ለ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ።
ሐ ፪ ኔፊ ፪፡ ፳፣ ፱፡ ፱፣ አልማ ፯፡ ፲፪፣ ፲፭፡ ፻፱–፻፲፣ ፲፪፡ ፳፭–፳፭፣ ሔለ. ፲፡ ፲፭–፲፳፣ ሞር. ፱፡ ፲፫።

ጣል፤ እናም የሙታን ትንሳኤ ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር ፊት ᵐመልሶ ያመጣል፤ እን ደዚህ በፍትህና በህግ መሰረት በስራቸው ᵐሊፈረድባቸው ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት ደግመው ይመለሳሉ።

፳፱ እነሆም፣ ፍትህ የግድ ጥያቄውን ሁሉ ይጠቀማል፣ እናም ደግሞ ምህረት የራሷ የሆነውን በሙሉ የእራሷ ታደርጋለች፤ እናም በእውነት ንስሃ ከገባው በቀር ማንም አይድንም።

፴ ምህረት ᵐፍትህን ይነጥቃል ብለህ ትገምታለህ? እኔ ግን እላለሁ፣ ቅንጣትም እንኳን ያህል ቢሆን አይሆንም። እንዲህ ከሆነ፣ እግዚአብሔር አምላክነቱን ያቆ ማል።

፴፩ እናም እግዚአብሔር ᵐከዓለም መፈ ጠር ጀምሮ ያዘጋጀውን ታላቁንና ዘለአ ለማዊ ᶮዓላማውን እንዲሆን እንደዚህም አድርጓል። በዚህ አይነት የሰዎች ቤዛነትና መዳን፣ እናም ደግሞ መጥፊያቸውና መከ ራቸው እንደዚህም መጣ።

፴፪ ስለዚህ ልጄ ሆይ፣ ᵐማንም የሚመጣ ቢሆን ይምጣና ከህይወት ውኃ በነፃ ይካ ፈል፤ እና የማይመጣውም ግን እንዲመጣ አይገደድም፤ ነገር ግን በመጨረሻው ቀን ᶮእንደስራው በእራሱ ላይ ᵒበድጋሚ ይመ ለሳል።

፴፫ ᵐመጥፎ ማድረግን ከፈለገ፣ እናም በጊዜው ንስሃ ካልገባ፣ እነሆ፣ በእግዚአ ብሔር ደግሞ መመለስ መሰረት መጥፎው ነገር በእርሱ ላይ ይደረግበታል።

፴፬ እናም አሁን ልጄ፣ እነዚህ ነገሮች ከእንግዲህ እንዳያስቸግሩህ እፈልጋለሁ፤ እናም ኃጢያትህ ብቻ በዚያ ወደ ንስሃ በሚ ያመጣህ ጭንቀት ያስጨንቅህ።

፴ ልጄ ሆይ፣ ከእንግዲህ ወዲያ የእግዚአ ብሔርን ፍትህ እንድትክድ አልፈልግም። ለራስህም የእግዚአብሔርን ፍትህ በመካድ ለእያንዳንዱ ጥልቅ ነገር በኃጢያትህ ምክ ንያት ለመስጠት አትጣር፤ ነገር ግን የእ ግዚአብሔር ፍትህ፣ እንዲሁም ምህረቱ፣ እናም ፅናቱ በልብህ በሙላት ተፅዕኖ እንዲ ያደርግ ፍቀድ፤ እናም ይህ ᵐበትህትና ወደ ምድር ያምጣህ።

፴፮ እናም እንግዲህ ልጄ ሆይ፣ ለዚህ ህዝብ ቃሉን ለመስበክ በእግዚአብሔር ተጠርተሃል። እናም አሁን ልጄ፣ መን ገድህን ተጓዝ፣ ታላቁ የምህረት ዕቅድም በእነርሱ ላይ ባለቤትነት እንዲኖረው ነፍ ሳትን ለንስሃ ታመጣ ዘንድ፣ ቃሉን በእው ነትና በጥሞና አውጅ። እናም እግዚአብሔር እንደቃሉ ይሰጥህም ዘንድ ይሁን። አሜን።

ምዕራፍ ፴፫

አልማ እና ልጆቹ ቃሉን ሰበኩ—ዞራሞ ውያን እና ሌሎች ተቃዋሚ ኔፋውያን ላማናውያን ሆኑ—ላማናውያን በኔፋዉ ያን ላይ ለጦርነት መጡባቸው—ሞሮኒ ኔፋውያንን በሚከላከል ጥሩር አስታጠ ቃቸው—ጌታ ለአልማ የላማናውያንን የጦር ስልት አሳየው—ኔፋውያን፣ ቤቶ ቻቸውን፣ ነፃነታቸውን፣ ቤተሰቦቻቸውን እና ኃይማኖታቸውን ተከላከሉ—የሞሮኒ እና የሌሂ ሠራዊት ላማናውያንን ከበቡአ ቸው። በ፳፱ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም አሁን እንዲህ ሆነ የአልማ ልጆች ቃሉን ለማወጅ በህዝቡ መካከል ሄዱ። እናም አልማ፣ እራሱ ደግሞ ማረፍ አል ቻለምና፣ ደግሞ ወደፊት ተጓዘ።

፪ አሁን በትንቢቱ መንፈስና ራዕይ አማ ካኝነት ቃሉንና እውነትን ከመስበካቸው ውጪ ስለስብከታቸው ከዚህ የበለጠ ምንም የምንለው አይኖርም፤ እናም በተጠሩበት

፳፫ መ አልማ ፵፡ ፳፩–፳፱።
ሠ ቅ.መ.መ. ፍርድ፣ የመጨረሻው።
፳፭ ሀ ቅ.መ.መ. ፍትህ።
፳፮ ሀ አልማ ፲፫፡ ፫፣ ፫ ኔፊ ፩፡ ፲፩።
ለ ፪ ኔፊ ፪፡ ፲፩–፴፣ ሙሴ ፩፡ ፴፱።
፳፯ ሀ አልማ ፭፡ ፴፪፣ ሔለ. ፲፩፡ ፴።
ቅ.መ.መ. ነጻ ምርጫ።
ለ ኢሳ. ፶፱፡ ፲፰፣ ራዕ. ፳፡ ፲፪።
ሐ አልማ ፵፩፡ ፲፭።
፳፰ ሀ አልማ ፵፩፡ ፪–፭።
፴ ሀ ቅ.መ.መ. ትሁት፣ ትሕትና።

ᵐበቅዱሱ የእግዚአብሔር ሥርዓት መሠ
ረት ሰበኩ።

፲ እናም አሁን በመሳፍንቱ አገዛዝ በአ
ስራ ስምንተኛው የንግስ ዘመን በኔፋውያ
ንና በላማናውያን መካከል ስለነበረው የጦ
ርነት ታሪክ እመለሳለሁ።

፲፩ እነሆም፣ እንዲህ ሆነ ᵐዞራማውያን
ላማናውያን ሆኑ፤ ስለዚህ፣ በአስራ ስምን
ተኛው ዓመት መጀመሪያ ላይ የኔፋውያን
ሕዝቦች ላማናውያን በእነርሱ ላይ ሲመጡ
ተመለከቱ፤ ስለዚህ ለጦርነት ተዘጋጁ፤
አዎን፣ ወታደሮቻቸውንም በኢየርሾን
ምድር በአንድ ላይ ሰበሰቡ።

፲፪ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን ከሺህ
ወታደሮቻቸው ጋር መጡ፤ እናም የዞራማ
ውያን ምድር ወደሆነችው ወደ አንቲዮኑም
ምድር መጡ፤ እናም ዜራሔምና ተብሎ
የሚጠራው ሰውም መሪያቸው ነበር።

፲፫ እናም አሁን፣ አማሌቂውያን ከላማና
ውያን የበለጡ ኃጢአተኞችና የገዳይ ፀባይ
ያላቸው በመሆናቸው፣ ስለዚህ፣ ዛራሄም
ናህ በላማናውያን ላይ ዋና ሻምበልን ሾመ፣
እናም ሻምበሎቹ በሙሉ አማሌቂውያንና
ዞራማውያን ነበሩ።

፲፬ አሁን እርሱ ይህንን ያደረገው በኔፋው
ያን ላይ ያላቸውን ጥላቻ ይጠብቁት ዘንድ፣
እነርሱም የእርሱን ዕቅድ ይፈፅሙ ዘንድ
በቁጥጥሩ ስራ ያደርጋቸው ዘንድ ነው።

፲፭ እነሆም፣ የእርሱ ዓላማ ላማናውያን
በኔፋውያን ላይ በቁጣ እንዲነሳሱ ነበር፤
ይህንም ያደረገው በእነርሱም ላይ ታላቅ
ኃይልን በግድ ይወስድ ዘንድ፣ እናም ደግሞ
ኔፋውያንን በምርኮ ስር በማምጣት በእነርሱ
ላይ ኃይል ያገኝ ዘንድ ነው።

፲፮ እናም አሁን የኔፋውያን ዓላማ ከጠላቶ
ቻቸው እጅ ይጠብቋቸው ዘንድ ምድራቸ
ውንና፣ ቤታቸውን፣ እንዲሁም ᵐሚስቶ
ቻቸውንና፣ ልጆቻቸውን ለመደገፍ ነበር፣
እናም ደግሞ እግዚአብሔርን እንደ ፍላ
ጎቶቻቸው ያመልኩ ዘንድ፣ ልዩ መብቶ
ቻቸውንና ጥቅሞቻቸውን፣ አዎን፣ እናም
ደግሞ ᶜነፃነታቸውን ይጠብቁ ዘንድ ነበር።

፲፯ በላማናውያን እጅ ቢወድቁ፣ ላማና
ውያን እውነተኛና ህያው የሆነውን አም
ላክ እግዚአብሔርን በእውነትና ᵐበመንፈስ
ᶜየሚያመልከው ማንኛውም እንደሚያጠፉ
ያውቃሉና።

፲፰ አዎን፣ እናም ደግሞ የአሞን ህዝብ
ተብለው በሚጠሩት ᵐወንድሞቻቸው በአ
ንቲ-ኔፊ-ሌሂዎችን ህዝብ ላይ ላማናውያን
የከፋ ጥላቻ እንዳላቸው ያውቃሉ—እናም
እነርሱ የጦር መሳሪያን አያነሱም፣ አዎን፣
ቃል ኪዳንን ገብተዋል እና ይህንንም አያ
ፈርሱም—ስለዚህ፣ እነርሱ በላማናውያን
እጅ ከወደቁ ይጠፋሉ።

፲፱ እናም ኔፋውያን እነርሱ እንዲጠፉ
አልፈለጉም፤ ስለዚህ የውርስ ምድርንም
ሰጡአቸው።

፲፲ እናም የአሞን ህዝብ ለኔፊ ህዝብ ወታ
ደሮቻቸውን ለመርዳት ካሉአቸው ነገር
አብዛኛውን ሰጡአቸው፤ እናም ኔፋውያን
ብቻ የላማንና ልሙኤል ዝርያ ቅንጅት የሆ
ኑትን ላማናውያንና፣ የእስማኤል ልጆች
የሆኑትን፣ እንዲሁም አማሌቂውያንና
ዞራማውያን ከነበሩትና፣ እም ከኔፋውያን
የተገነጠሉት በሙሉ፣ እናም ከኖህ ካህናት
ᵐዝርያ የሆኑትን እንዲቋቋሙ ተገደዱ።

፲፳ እንግዲህ የእነርሱ ዝርያዎችም ቁጥራ
ቸው እንደኔፋውያን የበዛ ነበር፤ እናም ኔፋ
ውያን ደም እስከማፍሰስ ድረስ ከወንድሞቻ
ቸው ጋር እንዲጣሉ እንዲህ ይገደዱ ነበር።

፲፳፩ እናም እንዲህ ሆነ የላማናውያን ወታ
ደሮች በአንቲዮኑም ምድር በአንድ ላይ
እንደተሰበሰቡ፣ እነሆ፣ የኔፋውያን ሠራ
ዊትም በኢየርሾን ምድር እነርሱን ለመገ
ናኘት ተዘጋጅተው ነበር።

፴፫ ፪ ሀ ቅ.መ.መ. የመልከ ጼዴቅ ክህነት።
፴ ሀ አልማ ፴፭፡፪–፲፴፣ ፴፪፡፡
፴፪ ሀ አልማ ፴፭፡፲፣ ፴፮፡፡
ለ ቅ.መ.መ. ክህነት።
፲ ሀ ዮሐ. ፴፡ ፳፫–፳፴።
ለ ቅ.መ.መ. ማምለክ።
፲፩ ሀ አልማ ፴፯፡፭፣ ፴፮፡፡
ለ ቅ.መ.መ. መብት።
፲፪ ሀ አልማ ፴፰፡፩–፫፣ ፭፣ ፳፣ ፳፭፡፩፣ ፲፫፣ ፳፯፡፪፣ ፳፭–፳፮።
፲፫ ሀ አልማ ፳፭፡፬።

፲፯ እንግዲህ፣ የኔፋውያን መሪ፣ ወይንም በኔፋውያን ላይ ዋና ሻምበል በመሆን የተ ሾመው—ዋናው አዛዥ የኔፋውያንን ሠራ ዊት በሙሉ የሚያዛቸው—እናም ስሙ ሞሮኒ ነበር፤

፲፰ እናም ሞሮኒ በኔፋውያን ወታደሮች ላይ ሙሉ በሙሉ አዛዥና የጦርነቱ አመ ራር ሰጪ ሆነ። እናም እርሱ በኔፊ ወታደ ሮች ላይ ዋና ሻምበል ሆኖ በተሾመበት ጊዜ ሀያ አምስት ዓመቱ ነበር።

፲፱ እናም እንዲህ ሆነ በኢየርሾን ዳርቻ ከላማናውያን ጋር ተገናኘ፤ እናም ህዝቡ በጎራዴና፣ በሻሙላና በሁሉም ዓይነት የጦር መሳሪያዎች ታጠቁ።

፲፳ እናም የላማናውያን ወታደሮች የኔ ፊን ህዝብ ወይንም፣ ሞሮኒ ህዝቡን በደ ረት ኪስና በእጅ የሚያዝ ጋሻ እንዳዘጋ ጃቸው በተመለከቱ ጊዜ፤ አዎን፣ እናም ደግሞ እራሳቸውን ለመከላከል ጋሻና ደግሞ ወፍራም ልብስ ለብሰው ነበር—

፳ እንግዲህ የዜራሔምና ሠራዊት በእ ንደዚህ ዓይነት ነገር አልተዘጋጁም ነበር፤ እነርሱ ጎራዴ እናም ሻምላቸው፣ ቀስትና ወስፈንጥሮቻቸውና፣ ድንጋይና ወንጭፎ ቻቸው ብቻ ነበሩአቸው፤ በወገባቸው ላይ ከታጠቁት ቆዳ በስተቀር ᵐእርቃናቸውን ነበሩ፤ አዎን ከዞራማውያንና ከአማሌቂ ውያን በስተቀር ሁሉም እርቃናቸውን ነበሩ፤

፳፩ ነገር ግን በደረት ኪስም ሆነ በጋሻ አልታጠቁም ነበር—ስለዚህ፣ ምንም እን ኳን ብዛታቸው ከኔፋውያን የበለጠ ቢሆ ንም ኔፋውያን ባሉአቸው የጦር መሳሪያዎች የተነሳ እጅግ ፈርተዋቸው ነበር።

፳፪ እነሆ፣ እንግዲህ እንዲህ ሆነ በኢ የርሾን ዳርቻ በኔፋውያን ላይ ለመዋጋት አልደፈሩም፤ ስለዚህ ከአንቲዮኑም ምድር ወደ ምድረበዳው ሸሹ፣ እናም ወደ ማንቲ ምድር ይመጡና ምድሪቱንም ይወስዱ ዘንድ በሲዶም ወንዝ በኩል በምድረበዳው ጉዞአቸውን አደረጉ፤ ምክንያቱም የሞሮኒ ወታደሮች ወዴት እንደሚሄዱ ያውቃሉ ብለው አልገመቱም ነበር።

፳፫ ነገር ግን እንዲህ ሆነ፣ ወደ ምድ ረበዳው ወዲያው እንደሄዱ ሞሮኒ የጦር ሰፈራቸውን እንዲመለከቱ በምድረበዳው ሰላዮችን ላከ፤ እናም ሞሮኒ ደግሞ የአል ማን ትንቢት በማወቁ፣ የኔፋውያን ወታደ ሮች እራሳቸውን ከላማናውያን ለመከላከል ᵐወዴት መሄድ እንዳለባቸው ጌታን ለመ ጠየቅ በመፈለጉ ወደ አልማ ሰዎችን ላከ።

፳፬ እናም እንዲህ ሆነ የጌታ ቃል ወደ አልማ መጣና፣ ደካማ በሆነው ክፍል ህዝ ብን ለማጥቃት ይጀምሩ ዘንድ የላማናው ያን ሠራዊት ወደ ማንቲ ምድር ለመምጣት በምድረበዳው በኩል እየተመሙ እንዳለ ለሞሮኒ መልዕክተኞች አልማ አስታወቀ። እናም መልዕክተኞቹ ሄዱና፣ መልዕክቱን ለሞሮኒ ተናገሩ።

፳፭ እንግዲህ ሞሮኒ፣ በማንኛውም መን ገድ ላማናውያን መጥተው ከተማውን እን ዳይወስዱ ዘንድ፣ ከወታደሮቹ የተወሰኑ ትን በኢየርሾን ምድር በመተው የቀሩ ትን ወታደሮቹን ወሰደ እናም ወደ ማንቲ ምድር ሄደ።

፳፮ እናም ሞሮኒ በዚያ ስፍራ ያሉት ሰዎች በሙሉ ምድራቸውንና ሀገራቸውን፣ መብ ታቸውን፣ እና ነፃነታቸውን ᵐለመጠበቅ ከላማናውያን ጋር እንዲዋጉ በአንድ ላይ እንዲሰባሰቡ አደረገ፤ ስለዚህ ላማናውያን ለሚመጡበት ጊዜም ተዘጋጅተው ነበር።

፳፯ እናም እንዲህ ሆነ ሞሮኒ በምድ ረበዳው በሲዶም ወንዝ በስተምዕራብ በኩል በነበረው በሲዶም ወንዝ ዳርቻ አጠገብ ባለው ሸለቆ ወታደሮቹ እንዲደ በቁ አደረገ።

፳፰ እናም ሞሮኒ የላማናውያን ወታደሮች የሚመጡበትን ጊዜ ያውቅ ዘንድ በዙሪያው ሰላዮችን አስቀመጠ።

፳፱ እናም እንግዲህ፣ ሞሮኒ የላማናውያ ንን ፍላጎት ስለሚያውቅ፣ ስለዚህ በምድሪ ቱም ላይ ለራሳቸው መንግስትን ያቋቋሙ

ዘንድ ወንድሞቻቸውን ማጥፋት እናም በባ
ርነት ስር ማድረግ ፍላጎታቸው ነበር፤
፴ እናም ደግሞ ምድራቸው፣ ″ነፃነታቸ
ውን እና ቤተክርስቲያናቸውን መጠበቅ የኔ
ፋውያን ፍላጎት ብቻ መሆኑን በማወቁ፣
ስለዚህ በስልት እነርሱን መከላከል ኃጢ
ያት አይደለም በማለት አሰበ፤ ስለዚህ፣
በሰላዮቹ አማካኝነት ላማናውያን የትኛ
ውን መንገድ እንደሚወስዱ አወቀ።
፴፩ ስለዚህ፣ ሞሮኒ ወታደሮቹን ከፈለ፣
እናም ግማሹን ወደ ሸለቆው ወሰደና፣ በስ
ተምስራቅ፣ እናም በሪፕላ ኮረብታ በስተ
ደቡብ ሸሸጋቸው፤
፴፪ እናም የቀሩትን በሲዶም ወንዝ በስ
ተምዕራብ በኩል፣ እናም በማንቲ ምድር
በታችኛው ዳርቻ በኩል ደበቃቸው።
፴፫ እናም እንደፍላጎቱ ወታደሮቹን
ካስቀመጠ በኋላ፣ ላማናውያንን ለመገና
ኘት ተዘጋጅቶ ነበር።
፴፬ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን ግማሾቹ
የሞሮኒ ወታደሮች በተደበቁበት ስፍራ በኮ
ረብታው በስተሰሜን በኩል መጡ።
፴፭ እናም ላማናውያን ሪፕላ ኮረብታን
ሲያልፉና፣ ወደ ሸለቆው ሲመጡ፣ እናም
የሲዶምን ወንዝ መሻገር እንደጀመሩ፣
″ሌሂ በተባለው ሰው የተመሩት በስተደ
ቡብ በኮረብታው የተሸሸጉት ወታደሮች
ወደፊት መጓዝ ጀመሩ፤ እናም በስተምስ
ራቅ ላማናውያንን ከበስተኋላቸው እንዲከ
ቡአቸው አደረገ።
፴፮ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን ኔፋ
ውያን ከበስተኋላቸው እንደመጡባቸው
በተመለከቱ ጊዜ፣ ወደ እነርሱ ተመለሱ፣
እናም ከሌሂ ሠራዊት ጋር መዋጋት ጀመሩ።
፴፯ እናም ሞትም በሁለቱም ወገን ተጀ
መረ፣ ነገር ግን በላማናውያን በኩል ይበል
ጡን አሰቃቂ ነበር፣ ምክንያቱም ″እርቃና
ቸው በእያንዳንዱ ምት የሞት ስራን በሚ
ያመጡት በኔፋውያን ጎራዴ እናም ሻሙላ
ከባድ ምት ተጋልጦ ነበር።
፴፰ በሌላ መልኩ፣ ኔፋውያን ″በደረት
ኪሳቸው፣ እናም በእጅ በሚያዙት ጋሻዎ
ቻቸው፣ እናም በራስ ቆባቸው የሰውነታ
ቸውን አስፈላጊ ቦታዎች በመከላከላቸው
ወይም ከላማናውያን ምት የሰውነታቸውን
አስፈላጊ ቦታዎች በመከላከላቸው፣ እን
ዳንዴ ከኔፋውያን መካከል በላማናውያን
ጎራዴዎችና ደም በመፍሰስ ምክንያት የሚ
ወድቁ ነበሩ።
፴፱ እናም እንዲህ ሆነ፣ ላማናውያን በመ
ካከላቸው በነበረው ታላቅ ጥፋት የተነሳ ወደ
ሲዶም ወንዝ እስከሚሸሹም ድረስ ፈሩ።
፵ እና እነርሱም በሌሂና በሰዎች እየተሳ
ደዱ ነበር፤ በሌሂም አማካኝነት ወደ ሲዶም
ውኃ ተገፉና፣ የሲዶምን ውኃ ተሻገሩ።
እናም ሌሂ እነርሱ የሲዶምን ወንዝ እንዳ
ይሻገሩ ወታደሮቹን በወንዙ ዳርቻ እንዲ
ቆዩ አደረገ።
፵፩ እናም እንዲህ ሆነ በሲዶም ወንዝ በሌ
ላኛው በኩል ሞሮኒና ወታደሮቹ ላማናውያ
ኖችን አገኙአቸው፣ እናም እነርሱን ማጥ
ቃትና መግደል ጀመሩ።
፵፪ እናም ላማናውያን ከሞሮኒ ሠራዊት
ፊት ወደማንቲ በድጋሚ ሸሹ፤ እናም በድ
ጋሚ ከሞሮኒ ወታደሮች ጋር ተገናኙ።
፵፫ እንግዲህ በዚህ ሁኔታ ላማናውያን
በኃይል ተዋጉ፤ አዎን ላማናውያን ከመ
ጀመሪያው ጀምሮም እንኳን ቢሆን በታላቅ
ብርታትና ድፍረት እንደዚህ ሲዋጉ በጭ
ራሽ አይታወቅም ነበር።
፵፬ እናም ላማናውያን በዋና ሻምበሎቻ
ቸውና መሪዎቻቸው በነበሩት ″በዞራማ
ውያን እና አማሌቂውያን፣ እንዲሁም ዋና
ሻለቃቸው በነበረውና፣ ዋና መሪና አዛዣ
ቸው በሆነው ዛራሄምናህ ተቀስቅሰው ነበር፤
አዎን፣ እንደዘንዶ ተዋጉ፣ ብዙ ኔፋውያ
ንም በእጃቸው ተገደሉ፤ አዎን፣ የራስ
ቆባቸውን መትተው ሁለት ቦታ ከፈሉባ
ቸው፣ እናም የደረት ኪሶቻቸውን በሱባ
ቸው፣ ብዙዎችን እጆቻቸውንም ቆረጡ

፴ ሀ አልማ ፵፯፡ ፲፪፣ ፴፭።
፴፭ ሀ አልማ ፵፱፡ ፲፯።
፴፭ ሀ አልማ ፵፡ ፭።
፴፯ ሀ አልማ ፵፫፡ ፭–፱።
፴፰ ሀ አልማ ፵፡ ፲–፲፭።
፵፩ ሀ አልማ ፵፫፡ ፯።

ባቸው፤ እናም ላማናውያኑ በኃያሉ ቁጣ ቸው እንደዚህ መቱአቸው።

፯፭ ይሁን እንጂ፣ ኔፋውያን የተነሳሱት በተሻለ ምክንያት ነበር፣ ምክንያቱም እነ ርሱ ᵐየሚዋጉት ለንግስናም ሆነ ለስልጣን ሳይሆን፣ ለሀገራቸውና ᵃለነፃነታቸው፣ ለሚስቶቻቸውና ለልጆቻቸው እናም ላሉ ዋቸው ነገሮች ሁሉ፣ አዎን ለሚያመልኩ በት ስርዓትና ለቤተክርስቲያናቸው ነበር።

፯፮ እናም ኔፋውያን ለአምላካቸው ይገባ ዋል ብለው የሚሰማቸውን ᵐስራ ነበር የሰ ሩት፤ ምክንያቱም ጌታ ለእነርሱ እናም ደግሞ ለአባቶቻቸው እንዲህ ብሎአቸው ነበርና፥ ᵃለመጀመሪያውም ሆነ ለሁለተ ኛው ጥፋት ተጠያቂዎች እስካልሆናችሁ ᵐድረስ በጠላቶቻችሁ እጅ እንድትገደሉ አትፍቀዱ።

፯፯ እናም በድጋሚ ጌታ እንዲህ አለ፥ ቤተሰቦቻችሁን እስከደም ጠብታ ᵐመከላ ከል ትችላላችሁ። ስለዚህ ኔፋውያን እራ ሳቸውን፣ ቤተሰቦቻቸውንና ምድራቸ ውን፣ እናም ሀገራቸውንና፣ መብታቸው ንና ኃይማኖታቸውን ለመጠበቅ ከላማናው ያን ጋር ተዋጉ።

፯፰ እናም እንዲህ ሆነ የሞሮኒ ሰዎች የላ ማናውያንን ኃያልነትና ቁጣ በተመለከቱ ጊዜ፣ በመፍራትና በመሸማቀቅ በፊታቸው ለመሸሽ ሊጀመሩ ነበር። እናም ሞሮኒ የእ ነርሱን ፍላጎት ተረዳና ቃሉን ወደ እነርሱ ላከና፣ በእንደዚህ ዓይነቱ ሀሳብ ልባቸ ውን፣ አዎን፣ የምድራቸውን፣ የነፃነታቸ ውን፣ አዎን፣ ከባርነት ነፃ የመውጣታቸ ውን ሀሳብንም ቀሰቀሰ።

፯፱ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያንን ተመ ልሰው አጠቁና፣ ወደ ጌታ ወደ አምላካቸው ለነፃነታቸውና ከባርነት እንዲለቀቁ በአንድ ድምፅ ᵐጮሁ።

፰ እናም ላማናውያንን በኃይል መቋቋማ ቸውን ጀመሩ፤ እናም በዚሁ ሰዓት ለነፃነታ ቸው ወደ ጌታ ጮሁ፣ ላማናውያንም ከፊ ታቸው መሸሽ ጀመሩ፤ እናም ወደ ሲዶም ውኃም ሸሹ።

፰፩ እንግዲህ፣ ላማናውያን በቁጥር ብዙ ነበሩ፤ አዎን፣ ከኔፋውያን በቁጥር እጥፍ ያህል ነበሩ፤ ይሁን እንጂ በሲዶም ወንዝ ዳርቻ በሸለቆው በአንድነት እስኪሰባሰቡ ተሰደዱ።

፰፪ ስለዚህ የሞሮኒ ወታደሮች ላማናውያ ንን ከሞላ ጎደል ከበቡአቸው፤ አዎን፣ በወ ንዙ በሁለቱም በኩል፣ እነሆ፣ በስተምስራ ቅም የሌሂ ሰዎች ነበሩና።

፰፫ ስለዚህ ዜራሔምና የሌሂን ሰዎች በሲዶም ወንዝ በስተምስራቅ፣ እናም የሞ ሮኒን ወታደሮች በሲዶም ወንዝ በስተምዕ ራብ፣ በኔፋውያን መከበባቸውን በተመለ ከቱ ጊዜ በፍርሃት ተውጠው ነበር።

፰፬ እንግዲህ፣ ሞሮኒ ፍርሃታቸውን በተ መለከተ ጊዜ የደም መፍሰሱ እንዲቆም ህዝ ቡን አዘዘ።

ምዕራፍ ፯፩

ሞሮኒ ላማናውያን ከኔፋውያን ጋር ሰላም እንዲፈጥሩ አለበለዚያም እንዲጠፉ ቃል ኪዳን እንዲገቡ አዘዘ—ዛራሄምናህ የቀረ በውን ሀሳብ ተቃወመ፣ እናም ጦርነቱም ቀጠለ—የሞሮኒ ወታደሮች ላማናውያንን አሸነፉ። ከ፳፩–፳፫ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ እነርሱም አቆሙና እርምጃቸውን ፈቀቅ አሉላቸው። እናም ሞሮኒ ለዛራሄምናህ እንዲህ አለው፥ እነሆ ዛራሄምናህ፣ እኛ የደም ሰዎች መሆን ᵐአን ፈልግም። እናንተ በእኛ እጅ ውስጥ መሆ ናችሁን ታውቃላችሁ፤ ይሁን እንጂ ልን ገድላችሁ አንፈልግም።

፪ እነሆ፣ ለስልጣን ስንል ደማችሁን

ᵃ፯፭ ᵇ አልማ ᵃ፯፩፥ ᶜ፭።
ᵃ ቅ.መ.መ. መብት።
ᵃ፯፮ ᵇ ቅ.መ.መ. ሁለንተና።
ᵃ ᶜ ኔፊ ᶜ፡ ᶜᶻᶻ፤
ᵃ ት. እና ቃ. ᶻᶻᶻ፥ ᶜᶻᶜ–ᶜᶻᶻ።
ᶜ ᵃ አልማ ᵃᶻᶻ፥ ᶜᶻᶻ፤
ᵃ ት. እና ቃ. ᶻᶻᶻ፥ ᶜᶻᶜ–ᶜᶻᶻ።
ᵃᶻᶻ ᵇ ት. እና ቃ. ᶻᶻᶻᶻ፥ ᶜᶻᶻ።
ᵃᶻᶻ ᵇ ዘፀአ. ᶻ፥ ᶜᶻᶜ–ᶜᶻᶻ፤ ሞዛያ ᶜᶻᶻ፣ ᶜᶻ።
ᵃᶻᶻ ᶻ ᵇ አልማ ᵃᶻᶜ፥ ᵃᶻᶻ።

እናፈሰው ዘንድ ከእናንተ ጋር ለመዋጋት አልመጣንም፤ ወይም ማናችሁንም በባር ነት ቀንበር ስር እንድናመጣችሁ አንፈል ግም። ነገር ግን ይህ እናንተ በእኛ ላይ የመ ጣችሁበት ዋናው ምክንያት ነው፤ አዎን፣ እናም በኃይማኖታችን የተነሳም በእኛ ላይ ተቆጥታችኋል።

፲ ነገር ግን አሁን፣ ጌታ ከእኛ ጋር መሆኑን ተመልክታችኋል፤ እናም እናንተንም በእኛ እጅ ስር እንድትሆኑ ማድረጉን ተመልክ ታችኋል። እናም አሁን ይህ በኃይማኖታች ንና በክርስቶስ ባለን እምነት መሆኑን እንድ ትገነዘቡ እፈልጋለሁ። እናም አሁን ይህንን እምነታችንን ማጥፋት እንደማትችሉ ትመ ለከታላችሁ።

፲፩ እንግዲህ ይህ እውነተኛ የሆነው የእ ግዚአብሔር እምነት መሆኑን ትመለከ ታላችሁ፣ አዎን በእግዚአብሔር በእ ርሱ፣ እናም በእምነታችንና፣ በኃይማኖ ታችን ታማኝ ሆነን እስከቆየን እንደሚረዳ ንና እንደሚጠብቀን እንዲሁም እንደሚያ ድነን ታያላችሁ፤ በመተላለፍ ካልወደቅን እናም እምነታችንን ካልካድን በቀር ጌታ እንድንጠፋ አይፈቅድም።

፲፪ እናም እንግዲህ፣ ዛራሄምናህ፣ በእም ነታችን፣ በኃይማኖታችንና [ሀ]በአምልኮአ ችን ስርዓት፣ እናም በቤተክርስቲያናችንና ለሚስቶቻችን፣ ለልጆቻችንም በምናደር ገው ቅዱስ ድጋፍ፣ ለምድራችንና ለሀገ ራችን ባለን የህልውና [ለ]ነፃነት፣ በእናንተ ላይ ኃይል እንድናገኝ ክንዳችንን ባበረ ታው አዎን፣ እናም ደግሞ የእግዚአብሔ ርን ቅዱስ ቃል በመጠበቅ ደስታችንን ሁሉ በምናገኝበት፤ እናም ከሁሉም በላይ በእኛ ዘንድ ይበልጥ በተወደደው በኃያሉ አምላክ ስም አዝሃለሁ—

፲፫ አዎን እናም ይህ ብቻም አይደለም፤ ለህይወት ባላችሁ ፍላጎቶች ሁሉ እንዲህ ስል አዛችኋለሁ፤ የጦር መሳሪያዎቻችሁን ሁሉ ለእኛ አስረክቡን፣ እናም እኛ የእናን ተን ደም አንፈልግም፣ ነገር ግን ተመልሳ ችሁ ከሄዳችሁና ለጦርነት በእኛ ላይ ዳግም ካልመጣችሁ ህይወታችሁን እናተርፍላች ኋለን።

፲፬ እናም አሁን፣ ይህንን ካላደረጋችሁ፣ እነሆ በእጃችን ናችሁ፣ እናም ህዝቤን እና ንተን እንዲያጠቁና፣ ከምድረ ገፅ እስከም ትጠፉ በሰውነታችሁ በሞት ቁስል እንዲ ያቁስሏችሁ አዛለሁ፤ ከዚያም በዚህ ህዝብ ላይ ማን ኃይል እንደሚኖረው እንመለከታ ለን፤ አዎን፣ ወደባርነት የሚመጣው ማን እንደሆነም እንመለከታለን።

፲፭ እናም አሁን እንዲህ ሆነ ዛራሄምናህ ይህንን አነጋገር በሰማ ጊዜ መጣና፣ ጎራዴ ውንም፣ ሻምላውንም፣ እና ቀስቱን፣ ለሞ ሮኒ በእጁ ሰጠውና፣ እንዲህ ሲል ተናገ ረው፥ የጦር መሳሪያዎቻችን እነሆ፣ መሳ ሪያዎቹን በሙሉ እንሰጣችኋለን፣ ነገር ግን እኛም ሆንን ልጆቻችን ልናፈርሰው እንደ ምንችል ስለምናውቅ [ሁ]መሃላ ልንወስድ አን ፈቅድም፤ ነገር ግን የጦር መሳሪያዎቻች ንን ውሰዱ፣ እናም ወደ ምድረበዳው እን ድንሄድ ዘንድ ፍቀዱልን፤ አለበለዚያ ግን ጎራዴዎቻችንን መልሰን እንይዛለንና እን ጠፋለን ወይንም እናሸንፋለን።

፲፮ እነሆ፣ የእኛ የእናንተ እምነት አባል አይደለንም፤ እግዚአብሔርም በእናንተ እጅ እንድንወድቅ እንዳደረገን አናም ንም፤ ነገር ግን ብልጠታችሁ ከጎራዴያ ችን እንደጠበቃችሁ እናምናለን። እነሆ፣ [ሁ]የደረት ኪሶቻችሁ እና ጋሻዎቻችሁ ጠብ ቀዋችኋል።

፲፯ እናም አሁን ዛራሄምናህ ንግግሩን እን ደጨረሰ፣ ሞሮኒ የተቀበለውን ጎራዴና የጦር መሳሪያዎች ወደ ዛራሄምናህ በመ መለስ እንዲህ ሲል ተናገረ፥ እነሆ፣ ጦርነ ቱን እንፈፅማለን።

፲፰ እንግዲህ የተናገርኳቸውን ቃላት መልሼ ልወስድ አልችልም፤ ስለዚህ ጌታ ህያው እንደሆነ፣ ለጦርነት በድጋሚ እን

[ሀ] ሆ ቅ.መ.መ. ስነስርዓቶች። [ለ] ሆ ቅ.መ.መ. መሀላ። [ሁ] ሆ አልማ ፵፫፡ ፴፰።

ዳትመለሱ በመሃላው ካልሄዳችሁ በቀር አትሄዱም። እናም በእጃችን ስለሆናችሁ ደማችሁን በመሬት ላይ እናፈሰዋለን፣ ወይንም ያቀረብኳቸውን ሀሳቦች ትቀበ ላላችሁ።

፲፫ እናም እንግዲህ ሞሮኒ እነዚህን ቃላት በተናገረ ጊዜ፣ ዛራሄምናህ ጎራዴ ውን መልሶ ያዘና፣ በሞሮኒ ተቆጥቶ ነበር፣ ሞሮኒንም ይገድለው ዘንድ ወደ እርሱ ዘንድ ሮጠ፤ ነገር ግን ጎራዴውን ባነሳ ጊዜ፣ እነሆ፣ ከሞሮኒ ወታደሮች አንዱ መታውና በመሬት ላይ ወደቀና፣ በእጆታው ተሰበረ፤ እናም ደግሞ የዛራሄምናህን አናት መትቶ ገሸለጠውና በመሬት ላይ ወደቀ። እናም ዛራሄምናህ ከእነርሱ ፊት ወደ ወታደሮቹ መካከል ሸሸ።

፲፬ እናም እንዲህ ሆነ በአጠገቡ ቆሞ የነ በረው፣ የዛራሄምናህን አናት የገሸለጠው፣ ቆቡን ከፀጉሩ ጋር ከመሬት ላይ አነሳውና፣ በጎራዴው ጫፍ ላይ አስቀመጠው፣ እናም ወደእነርሱም ከፍ አድርጎ በማሳየት በኃይል እንዲህ ሲል ጮኸ፥

፲፭ ይህ የአለቃችሁ ቆብ የሆነው በመሬት ላይ እንደወደቀ፣ የጦር መሳሪያዎቻችሁን ካልሰጣችሁን እናም በሰላም ለመሄድ ቃል ኪዳን ካልገባችሁ በቀር እንዲሁ በመሬት ላይ ትወድቃላችሁ።

፲፮ እንግዲህ ብዙዎች እነኚህን ቃላት በሰሙበት ጊዜ እናም በጎራዴው ላይ የነ በረውን ቆብም በተመለከቱ ጊዜ በፍር ሃት ተሞሉ፤ እናም ብዙዎች መጡና፣ የጦር መሳሪያዎቻቸውን በሞሮኒ እግር ስር ጣሉት፣ ″የሰላም ቃል ኪዳንን ገቡም። እናም ቃል ኪዳን የገቡት ሁሉ ወደ ምድ ረበዳው እንዲሄዱ ፈቀዱላቸው።

፲፯ እንግዲህ እንዲህ ሆነ ዛራሄምናህ እጅግ ተናደደ፣ እናም ቀሪዎቹ ወታደሮቹ ከኔፋውያን ጋር በኃይል እንዲጣሉ በቁጣ አነሳሳቸው።

፲፰ እናም እንግዲህ ሞሮኒ በላማናውያን ግትርነት የተነሳ ተቆጥቶ ነበር፤ ስለዚህ ህዝቡ እንዲወጉአቸውና እንዲገድላቸው አዘዘ። እናም እንዲህ ሆነ እነርሱን መግደል ጀመሩ፤ አዎን እናም ላማናውያን በጎራዴ ዎቻቸውና በኃይላቸው ተዋጉ።

፲፱ ነገር ግን እነሆ፣ የላማናውያን ባዶ ሰውነትና፣ ባዶ ራሶቻቸው ለኔፋውያን የሰሉ ጎራዴዎች ተጋልጠው ነበር፤ አዎን እነሆ ተበሳስተውና ተመትተው ነበር፣ አዎን፣ እናም በኔፋውያን ጎራዴዎችም ፊት በፍጥነት ይወድቁ ነበር፤ እናም የሞ ሮኒ ወታደር እንደተነበየም መወገድ ጀም ረው ነበር።

፲፱ እንግዲህ ዛራሄምናህ፣ እነርሱ በሙሉ ሊጠፉ መቃረባቸውን በተመለከተ ጊዜ፣ ቀሪውን ህይወታቸውን የሚያተርፉት ከሆነ፣ በድጋሚ ለጦርነት ወደ እነርሱ ″በጭራሽ እንደማይመጡ፣ እርሱ እናም ደግሞ ህዝቡ ቃል ኪዳን እንደሚገቡ ለሞ ሮኒ በኃይል በመጮህ ቃል ገባ።

፳ እናም እንዲህ ሆነ ሞሮኒ የሞት ስራ በህዝቡ መካከል በድጋሚ እንዲቆም አደ ረገ። የጦር መሳሪያዎችንም ከላማናውያን ወሰደ፤ እናም ለሰላም ″ቃል ኪዳን ከእርሱ ጋር ከገቡ በኋላ ወደ ምድረበዳው እንዲሄዱ ተፈቅዶላቸው ነበር።

፳፩ እንግዲህ የሞቱባቸው ቁጥር ብዙ በመሆኑ ሊቆጠር አይችልም ነበር፤ አዎን በኔፋውያንም ሆነ በላማናውያን በኩል የሚቆቹ ቁጥር እጅግ ብዙ ነበር።

፳፪ እናም እንዲህ ሆነ የሞቱባቸውን ወደ ሲዶም ወንዝ ጣሉአቸው፤ እናም ተወስደ ውና በባህሩ ጥልቅ ውስጥ ተቀብረው ነበር።

፳፫ እናም የኔፋውያንም ሆኑ የሞሮኒ ሠራ ዊት ተመለሱ፣ እናም ወደ ቤታቸውና ወደ ምድራቸው መጡ።

፳፬ እናም በኔፋውያን ላይ አስራ ስምንት ኛው ዓመት የመሣፍንት አገዛዝ በዚሁ ተፈ ፀመ። እናም በኔፊ ሰሌዳዎች ላይ የተፃፈው የአልማ ምዝገባም ተጠናቀቀ።

፲፭ ″ ፩ ኔፊ ፩፡ ፴፯፣ አልማ ፶፡ ፴፯።

፲፱ ″ አልማ ፴፯፡ ፮።

፳ ″ አልማ ፳፩፡ ፲፭–፲፯።

ሔለማን በዘመኑ ባስቀመጠው በምዝገባው መሰረት በሔለማን ዘመን የኔፊ ህዝብ የጦ ርነታቸው እና የፀባቸው ታሪክ።

ከምዕራፍ ፴፭ እስከ ፷፪ አጠቃሎ የያዘ።

ምዕራፍ ፴፭

ሔለማን የአልማን ቃላት አመነ—አልማ ስለኔፋውያን ጥፋት ተነበየ—እርሱም ምድሪቱን ባርኳታል፣ እናም ረግሟ ታል—አልማ ምናልባት እንደሙሴ በመ ንፈስ ተወስዷል—ፀብ በቤተክርስቲያኗ ውስጥ አደገ። በ፳፫ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እነሆ፣ አሁን እንዲህ ሆነ የኔፊ ህዝብ ጌታ በድጋሚ ከጠላቶቻቸው እጅ እንዲ ወጡ ስላደረጋቸው እጅግ ተደሰቱ፤ ስለ ዚህ ለጌታ ለአምላካቸው ምስጋናን አቀ ረቡ፤ አዎን፣ እናም [a]እጅግ ያሙና፣ ፀለ ዩም፣ እግዚአብሔርን እጅግ ታላቅ በሆነ ደስታ አመለኩትም።

፪ እናም እንዲህ ሆነ በኔፊ ሕዝብ በመሣ ፍንቱ የአስራ ዘጠነኛው የንግስ ዘመን ላይ አልማ ወደ ልጁ ሔለማን መጣ እናም እን ዲህ አለ፥ ስለተጠበቁት [b]መዝገቦች በተመ ለከተ የተናገርኳቸውን ቃላት ታምናለህን?

፫ እናም ሔለማን እንዲህ ሲል ተናገረው፥ አዎን አምናለሁ።

፬ እናም አልማ በድጋሚ እንዲህ አለ፥ በሚመጣው በክርስቶስ ታምናለህን?

፭ እናም እርሱ እንዲህ አለ፥ አዎን፣ የተ ናገርካቸውን ቃላት በሙሉ አምናለሁ።

፮ እናም አልማ በድጋሚ እንዲህ አለው፥ [c]ትዕዛዛቴን ትጠብቃለህን?

፯ እናም እርሱ እንዲህ አለ፥ አዎን፣ ትዕ ዛዛቶችህን በልቤ ሙሉ እጠብቃቸዋለሁ።

፰ ከዚያም አልማ እንዲህ አለው፥ አንተ የተባረክህ ነህ፤ እናም ጌታ በዚህች ምድር ላይ [d]እንድትበለፅግ ያደርግሃል።

፱ ነገር ግን እነሆ፣ ለአንተ በመጠኑ [e]የም ተነብየው ነገር አለኝ፤ ነገር ግን ለአንተ የም ተነብየውን ለሰዎች አታሳውቅ፤ አዎን፣ የምተነብይልህን ትንቢት እስከሚፈፀም ድረስ ማንም እንዲያውቀው አታድርግ፤ ስለዚህ የምነግርህን ቃላት ፃፍ።

፲ እናም ቃላቱ እነኚህ ናቸው፥ እነሆ፣ እነዚህ ህዝብ፣ ኔፋውያን፣ በውስጤ ባለው የራዕይ መንፈስ መሰረት፣ ኢየሱስ ክርስቶስ እራሱን ከገለፀላቸው [f]ከአራት መቶ ዓመ ታት በኋላ [g]እምነትን በማጣት እንደሚመ ነምኑ እመለከታለሁ።

፲፩ አዎን፣ እናም ከዚያም፣ የኔፊ ህዝብ [h]እስከሚጠፉም ድረስ፣ ጦርነትና ቸነፈርን ይመለከታሉ፤ አዎን፣ በመሃከላቸው ረሃብ እና የደም መፋሰስ ይሆናል—

፲፪ አዎን፣ ይህም የሆነው እምነት በማ ጣት በመመንመናቸውና በጨለማው ስራና [i]በአመንዝራነት፣ እናም በሁሉም ዓይ ነት ክፋቶች ላይ በመውደቃቸው ነው፤ አዎን፣ እንዲህ እልሃለሁ፣ በታላቁ ብር ሃንና ዕውቀት ላይ ኃጢያትን በመፈፀማ ቸው፤ አዎን፣ ይህ ታላቅ ክፋት ከመም ጣቱ በፊት አራተኛው ትውልድም ቢሆን አያልፍም እላችኋለሁ።

፲፫ እናም ያ ታላቁ ቀን ሲመጣ፣ እነሆ፣ አሁን ያሉት፣ ወይንም ከኔፊ ህዝብ ጋር አብረው የተቆጠሩት ወገኖች ከኔፊ ህዝብ ጋር [j]የማይቆጠሩበት ጊዜ በፍጥነት ይመ ጣል።

፲፬ ነገር ግን ማንም የተረፈ፣ እናም በዚያን ታላቁና ከአስፈሪው ቀን ያልጠፋ፣ የጌታ ደቀ መዝሙር ተብለው ከሚጠሩት ጥቂ ቶች በስተቀር፣ ከላማናውያን ጋር አብሮ [k]ይቆጠራልና፣ እንደ እነርሱም ይሆናሉ፤

፴፭ ፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. ጾም፣ መጾም።
፪ *ሀ* አልማ ፴፯፡ ፩–፭፤ ፶፡ ፴፰።
፮ *ሀ* ቅ.መ.መ. ታዛዥነት፣ ታዛዥ፣ መታዘዝ፤ የእግዚአብሔር ትእዛዛት።
፰ *ሀ* ፩ ኔፊ ፪፡ ፲፬፤ አልማ ፴፰፡ ፲፫–፲፮፤ ፳፭።
፱ *ሀ* ቅ.መ.መ. ትንቢት፣ መተንበይ።
፲ *ሀ* ፩ ኔፊ ፲፪፡ ፣–፲፭፤ ሔለ. ፲፫፡ ፱፤ ሞር. ፰፡ ፮–፯።
ለ ቅ.መ.መ. አለማመን፤ ክህደት።
፲፩ *ሀ* ዚረም ፩፡ ፣፤ ሞር. ፰፡ ፪–፫፣ ፮–፯።
፲፪ *ሀ* ቅ.መ.መ. ምኞት።
፲፫ *ሀ* ሔለ. ፫፡ ፣፲፯።
፲፬ *ሀ* ሞሮኒ ፱፡ ፳፭።

እናም ላማናውያን እነርሱን ^እስከሚጠፉ ድረስም እንኳን ያሳድዷቸዋል። እናም እንግዲህ፣ በኃጢያትም የተነሳ ይህ ትን ቢት ይፈፀማል።

፲፮ እናም አሁን እንዲህ ሆነ አልማ እነዚ ህን ነገሮች ለሔለማን ከተናገረ በኋላ፣ ባረ ከው፣ እናም ደግሞ ሌሎች ወንድ ልጆ ቹን ባረካቸው፤ ደግሞም *ለፃድቃኖች ሲል ምድሪቱን ባረካት።

፲፯ እናም እንዲህ አለ፥ ጌታም እንዲህ ይላል—አዎን፣ ይህች ምድር ጥፋት ለሚያ ደርጉት ለሁሉም ሀገር፣ ነገድ፣ ቋንቋና ህዝብ በሙሉ ሲበስሉ እንዲጠፉ ዘንድ ምድሪቱ *የተረገመች ትሁን፤ እናም እንደተናገርኩ ትም ይሆናል፤ ይህ ለምድሪቱ ^የእግዚአ ብሔር እርግማን እንዲሁም በረከት ነው፤ ምክንያቱም ጌታ ኃጢያትን ^በትንሹም ቢሆን ሊቀበለው አይቻለውምና።

፲፰ እናም እንግዲህ አልማ እነዚህን ቃላት በተናገረ ጊዜ *ቤተክርስቲያኗን ባረካት፤ አዎን፣ ከዚህ ጊዜም ጀምሮ በእምነት በመ ፅናት የቆሙትን በሙሉ ባረካቸው።

፲፱ እናም አልማ ይህንን ባደረገ ጊዜ፣ ወደ ሜሌቅ ምድር እንደሚሄድ በማድረግ፣ ከዛራሔምላ ምድር ወጣ። እናም እንዲህ ሆነ ከዚህም በኋላ ከእርሱ ምንም አልተ ሰማም ነበር፤ ስለሞቱም ሆነ ቀብሩ ምንም አላወቅንም።

፲፱ እነሆ፣ እርሱ ፃድቅ ሰው መሆኑን ይህን እናውቃለን፤ እናም በመንፈስ መወሰዱን ወይንም በጌታ እጅ እንደሙሴ *መቀበሩ በቤተክርስቲያን ይህ ንግግር ተሰራጨ። ነገር ግን እነሆ ቅዱሳት መጻሕፍት ጌታ ሙሴን ለራሱ ወሰደው ይላሉ፤ እናም አል ማንም ደግሞ በመንፈስ ወደ እርሱ ወስ ዶታል ብለን እንገምታለን፤ ስለዚህ በዚህ የተነሳ ስለአልማ ሞትም ሆነ ቀብር ምንም አናውቅም።

፳ እናም አሁን እንዲህ ሆነ በኔፊ ህዝብ ላይ በመሣፍንቱ የአስራ ዘጠነኛ ንግስና መጀመሪያ ላይ ሔለማን በህዝቡ መካከል ቃሉን ለማወጅ ሄደ።

፳፩ እነሆም ህዝቡ ከላማናውያን ጋር በመ ዋጋቱና፣ ትንሽ ፀብና ርበሻ በህዝቡ መካ ከል በመኖሩ፣ *የእግዚአብሔር ቃል በመ ካከላቸው መነገሩ አስፈላጊ እየሆነ፣ አዎን፣ እናም በቤተክርስቲያኗ ውስጥ ደንብ መቋ ቋሙ አስፈላጊ እየሆነ መጣ።

፳፪ ስለዚህ፣ ሔለማንና ወንድሞቹ በም ድሪቱ ላይ፣ አዎን፣ በምድሪቱ ላይ ባሉት በኔፊ ሰዎች በተያዙት ከተሞች ሁሉ ቤተክ ርስቲያኗን በድጋሚ ለማቋቋም ሄዱ። እናም እንዲህ ሆነ በምድሪቱ ላይ ባሉት በቤተክ ርስቲያኖቹ በሙሉ ካህናትን እና መምህራ ንን ሾሙአቸው።

፳፫ እናም አሁን እንዲህ ሆነ ሔለማንና ወንድሞቹ በቤተክርስቲያኖቹ ላይ ካህናት ንና መምህራንን ከሾሙ በኋላ በህዝቡ መካ ከል *ፀብ ተነሳ፣ እናም የሔለማንና የወን ድሞቹንም ቃላት አላዳመጡም።

፳፬ ነገር ግን በትዕቢት እያደጉ፣ እጅግ *ሀብታሞችም በመሆናቸው በልባቸው ኩራት እየተሞሉ ሄዱ፤ ስለዚህ በራሳቸው ^ግምት ከፍ ብለው በልፅገዋል፤ እናም በእግዚአብሔር ፊት በቅንነት ለመራመድ የሔለማንንና የወንድሞቹን ቃላት አላዳ መጡም።

ምዕራፍ ፵፮

አማሊቅያ ንጉስ ለመሆን አሴረ—ሞሮኒ የነፃነት አርማን አነሳ—ሕዝቡንም እምነ ታቸውን እንዲከላከሉ አነሳሳቸው—እው ነተኛ አማኞች ክርስቲያኖች ተብ ለው ተጠሩ—የዮሴፍ ቅሪቶች ይጠበ ቃሉ—አማሊቅያ እና የተገነጠሉት ወደ

፲፩ *ለ* ሞሮኒ ፩፡፩–፮።
፲፩ *ሀ* አልማ ፴፮፡፲፡ ፴፱፡፴።
፲፯ *ሀ* ፪ ኔፊ ፩፡፲፤ አልማ ፴፯፡፴፩፤ ኤተር ፪፡፳–፲፪።
ለ ት. እና ቃ. ፲፴፡፳፩።
ሐ ት. እና ቃ. ፩፡፴፩።
፲፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን።
፲፱ *ሀ* ቅ.መ.መ. የተቀየሩ ሰዎች።
፳፩ *ሀ* አልማ ፴፩፡፩።
፳፫ *ሀ* ፮ ኔፊ ፲፩፡፳፤ ፳፯–፳፱።
፳፬ *ሀ* ቅ.መ.መ. ሀብቶች።
ለ ቅ.መ.መ. ኩራት።

ኔፊ ምድር ሸሹ—የነፃነትን ጉዳይ የማ ይደግፉ እንዲሞቱ ተደረገ። ከ፳፫–፳፰ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ የሔለማንንና የወን ድሞቹን ቃላት መስማት ያልፈለጉት ሁሉ በወንድሞቻቸው ላይ በአንድነት ተሰባሰ ቡባቸው።

፪ እናም አሁን እነሆ፣ እነርሱም እስከ ሚገድሉአቸው ድረስ እጅግ ተቆጥተው ነበር።

፫ አሁን በወንድሞቻቸው ላይ ተቆጥተው የነበሩት መሪ ትልቅና ጠንካራ ሰው ነበር፤ እናም ስሙ አማሊቅያ ተብሎ ይጠራ ነበር።

፬ እናም አማሊቅያ ንጉስ መሆንን ይፈልግ ነበር፤ እናም የተቆጡት ሰዎችም ደግሞ እርሱ ንጉሳቸው እንዲሆንላቸው ይፈልጉ ነበር፤ እናም ብዙዎቹ በምድሪቱ *የበታች ዳኞች የነበሩ ናቸው፣ እነርሱም ስልጣንን ይፈልጉ ነበር።

፭ እናም እርሱን የሚረዱትና ንጉሳቸው እንዲሆን የሚያደርጉት ከሆነ በህዝቡ ላይ ገዢ አደርጋችኋለሁ ባላቸው በአማሊቅያ ሽንገላ ተመርተው ነበር።

፮ አዎን በቤተክርስቲያኗ ላይ ሊቀ ካህን ስለነበሩ፣ ምንም እንኳን ሔለማን እና ወን ድሞቹ ቢሰብኩም፣ አዎን፣ በቤተክርስቲ ያኗ ላይ ታላቅ እንክብካቤን ቢያደርጉም፣ በአማሊቅያ ወደ መገንጠል ተመሩ።

፯ እናም በቤተክርስቲያኗ የአማሊቅ ያን የሽንገላ ቃላት ያመኑ ብዙዎች ነበሩ፤ ስለዚህ ከቤተክርስቲያኗም እንኳን ተገነ ጠሉ፤ እናም ምንም እንኳን በላማናውያን ላይ ታላቅ *ድል ቢያገኙም፣ እና በጌታ እጅ በዳኑበት ደስታቸው እጅግ ታላቅ ቢሆንም፣ የኔፊ ህዝብ ሁኔታም እንደዚህ እጅግ የማያ ስተማምን እንዲሁም አደገኛ ነበር።

፰ ስለሆነም የሰው ልጆች ጌታ አምላካ ቸውን እንዴት *በፍጥነት እንደሚዘነጉ፣ አዎን፣ ክፋትን ለመሰራት፣ እናም በክፉ ሰዎችም ለመመራት እንዴት እንደሚፈ ጥኑ እንመለከታለን።

፱ አዎን፣ እናም አንድ ኃጢአተኛ ሰው በሰው ልጆች መካከል ለታላቅ *ኃጢያት መንስኤ ሊሆን እንደሚችል ደግሞ እንመ ለከታለን።

፲ አዎን፣ አማሊቅያ የብልጠት ዕቅድ ያለው በመሆኑና፣ ብዙ የሸንጋይ ቃላት ያሉት ሰው በመሆኑ፣ የብዙ ሰዎችን ልብ ክፋት እንዲሰሩ፣ አዎን፣ እናም የእግዚ አብሔርን ቤተክርስቲያንና፣ እግዚአብ ሔር የሰጣቸውን *የነፃነት መሰረት፣ ወይም *ለፃድቃን ሲል በምድር ገጽ ላይ እግዚአ ብሔር የላከውን በረከት ለማጥፋት እንደ ሚመራቸው እንመለከታለን።

፲፩ እናም አሁን እንዲህ ሆነ ሞሮኒ የኔፊ ሠራዊት *ዋና ሻምበል የነበረው፣ ይህንን ተቃውሞ በሰማ ጊዜ በአማሊቅያ ላይ ተቆ ጥቶ ነበር።

፲፪ እናም እንዲህ ሆነ ኮቱን ቀደደና፣ ቁራጩን ወስዶ በላዩ ላይ አምላካችንን፣ ኃይማኖታችንን፣ እናም ነፃነታችንንና፣ ሰላማችንን፣ እናም ሚስቶቻችንንና፣ ልጆ ቻችንን *ለማስታወስ በማለት ፃፈበትና በእ ንጨት ጫፍ ላይ አሰረው።

፲፫ እናም የራስ ቆቡንም፣ የደረት ኪሱ ንም፣ ጋሻውንም አሰረ፣ እናም በወገቡ ላይ ጥሩርን ታጠቀ፤ የተቀደደው ኮቱን ያደረ ገበትን እንጨትንም ወሰደ (እናም የነፃነት አርማ ብሎም ጠርቶታል) እናም በመሬት ላይ ሰገደና፣ የክርስቲያኖች ቡድን ምድ ሪቷን የራሳቸው እስካደረጉ ድረስ፣ የነፃ ነት በረከት በወንድሞቹ ላይ እንዲሆን ወደ አምላኩ በኃይል ፀለየ—

፲፬ እውነተኛ የክርስቶስ አማኞች የነበሩ፣ በእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን አባል የነ

፵፮ ፩ *ሀ ሞዛያ ፳፱፡ ፲፩፣ ፳፰–፳፱።
፪ *ሀ አልማ ፵፩፡ ፲፱–፳።
፫ *ሀ ሔለ. ፲፪፡ ፪፡ ፱–፲።
፬ *ሀ ሞዛያ ፳፱፡ ፲፯–፲፰።
፲ *ሀ ፪ ኔፊ ፩፡ ፯፣ ሞዛያ ፳፱፡ ፴፪።
ለ ፪ ኔፊ ፩፡ ፯።
፲፩ *ሀ አልማ ፵፫፡ ፲፯–፲፯።
፲፪ *ሀ ነህ. ፱፡ ፲፩፣ አልማ ፵፩፡ ፲።

በሩ፣ የቤተክርስቲያኗ ባልሆኑትም እንዲህ ተብለው ይጠሩ ነበርና።

፲፩ እናም የቤተክርስቲያኗ የነበሩት ታማኞች ነበሩ፣ አዎን የክርስቶስ እውነ ተኛ አማኞች የነበሩት በሙሉ ᵐየክርስቶ ስን ስም፣ ወይንም በሚመጣው ክርስቶስ በማመናቸው ᵃክርስቲያን ተብለው የሚ ጠሩበትን በደስታ ለብሰው ነበር።

፲፪ እናም ስለዚህ፣ በዚህ ጊዜ፣ ሞሮኒ የክ ርስቲያኖች ጉዳይና የምድሪቱ ነፃነትም ይበ ልጥ ሞገስን እንዲያገኝ ፀለየ።

፲፫ እናም እንዲህ ሆነ ነፍሱንም ለእግዚ አብሔር ባፈሰሰ ጊዜ፣ ᵐበወደመው ምድር በስተደቡብ ያሉትን ክፍሎች በሙሉ፣ አዎን፣ እናም በአጠቃላይ በምድሪቱ በሰሜን፣ በደቡብም ክፍል ያለውን በሙሉ ስም ሰጣቸው—የተመረጠች ምድርና የነፃ ነት መሬት በማለት ሰየመ።

፲፬ እናም እንዲህ አለ፥ በእርግጥ እኛ የክ ርስቶስን ስም በመልበሳችን የተጠላን በራሳ ችን መተላለፍን እስከምናመጣ ድረስ እን ድንዋረድ እንዲሁም እንድንጠፋ እግዚአ ብሔር አይፈቅድም።

፲፭ እናም ሞሮኒ እነዚህን ቃላት በተናገረ ጊዜ፣ የተቀደደውን ᵐልብሱን ከፍ በማድ ረግ በተቀደደው በኩል የተፃፈውን ሰዎች ሁሉ ያዩለት ዘንድ በአየር ላይ አወዛወዘው፣ እናም ድምፁን ከፍ በማድረግም እንዲህ በማለት ጮኸ፥

፲፮ እነሆ፣ ማንም ይህንን አርማ በምድሪቱ ላይ የጠበቀ በጌታ ብርታት መጥቶ ከእኔ ጋር ይሁን፣ እናም ጌታ እግዚአብሔር እንዲባ ርካቸው መብታቸው፣ እናም ኃይማኖታ ቸውን እንደሚጠብቁ ቃል ኪዳኑ ይግቡ።

፲፯ እናም እንዲህ ሆነ ሞሮኒ እነዚህን ቃላት ባወጀ ጊዜ፣ እነሆ፣ ሰዎቹም ልብ ሶቻቸውን ለምልክት በመቅደድ ወይንም ጌታ አምላካቸውን እንደማይተዉም ቃል በመግባት፣ ወይም በሌላ አነጋገር የእግዚ አብሔርን ትዕዛዛት የሚተላለፉ ወይንም በመተላለፍ የሚወድቁ ከሆነ እናም የክር ስቶስን ስም ለመልበስ ᵐየሚያፍሩ ከሆነ እነ ርሱ ልብሳቸውን እንደቀደዱ ጌታም እነር ሱን ይለያቸዋል በማለት የጦር መሳሪያዎ ቻቸውን በወገባቸው ላይ በመታጠቅ በአ ንድ ላይ በመሮጥ መጡ።

፲፰ እንግዲህ የገቡት ቃል ኪዳን ይህ ነበር፣ እናም ልብሳቸውንም በሞሮኒ እግር ስር በመጣል እንዲህ አሉ፥ በመተላለፍ የምንወድቅ ከሆነ በምድሪቱ በስተሰሜን እንደነበሩት ወንድሞቻችን እንደምንጠፋ ከአምላካችን ጋር ቃል ኪዳን ገብተናል፤ አዎን በመተላለፍ የምንወድቅ ከሆነ ልብ ሶቻችንን እንዲረገጡ በእግርህ ስር እንደጣ ልናቸው አምላካችንም እኛን በጠላቶቻችን እግር ስር እንድንወድቅ እንዲሁ ያድርገን።

፲፱ ሞሮኒ እንዲህ ሲል ተናገራቸው፥ እነሆ፣ እኛ የያዕቆብ ዘር ቅሪት ነን፣ አዎን፣ በወንድሞቹ ᵐኮቱ የተቀዳደዱበት ᵃየዮሴፍ ᵃዘር ቅሪት ነን፤ አዎን እናም አሁን እነሆ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ለመጠበቅ እና ስታውስ፣ አለበለዚያ ልብሶቻችን በወንድ ሞቻችን ይቀደዳሉ፣ እናም ወደ ወህኒ ቤት እንጣላለን፣ ወይንም እንሸጣለን፣ ወይንም እንገደላለን።

፲፳ አዎን፣ ነፃነታችንን እንደ ዮሴፍ ᵐቅሪት እንጠብቅ፤ አዎን ከመሞቱ በፊት የነበሩትን የያዕቆብን ቃላት እናስታውስ፣ እነሆም፣ የዮሴፍ ኮት ቅሪት ክፍል የሆ ኑት እንደተጠበቁና እንዳልበሰበሱም ተመለከተ። እናም እንዲህ አለ—የልጄ ልብስ ቁራጭ እንደተጠበቁ ሁሉ የልጄ ዘር ᵃቅሪቶች በእግዚአብሔር እጅ ይጠበ ቃሉ፣ እናም ወደ እርሱ ይወሰዳሉ፣ የዮ

፲፭ ሀ ሞዛያ ፭፡፣ ፯–፱።
ለ የሐዋ. ፲፭፡ ፳፯፤
፩ ጴጥ. ፪፡ ፲፯።
፲፯ ሀ አልማ ፳፪፡ ፴–፴፩።
፲፱ ሀ ቅ.መ.መ. ምልክት።
፳፩ ሀ ፩ ኔፊ ፰፡ ፳፩–፳፰፤
ሞር. ፰፡ ፴፰።
፳፫ ሀ ዘፍጥ. ፴፯፡ ፫፡ ፴፩–፴፯።
ለ ቅ.መ.መ. ዮሴፍ፣ የያዕቆብ ልጅ።
ሐ ዘፍጥ. ፵፱፡ ፳፪–፳፮፤
፩ ኔፊ ፭፡ ፲፱–፲፭።
፳፭ ሀ ዓም. ፭፡ ፲፭፤
፫ ኔፊ ፭፡ ፳፩–፳፪፤ ፲፡ ፲፯።
ለ ፪ ኔፊ ፫፡ ፭–፳፩፤
ኤተር ፲፫፡ ፯–፯።

ሴፍ ዘር ቅሪቶች ግን እንደ ልብሱ ቁራጭ ቅሪቶች ይጠፋሉ።

፳፭ እናም እነሆ፣ ይህ ነፍሴን ያሳዝና ታል፤ ይሁን እንጂ ወደ እግዚአብሔር በሚወሰዱ በእርሱ የዘር ክፍል ምክንያት ነፍሴ በልጄ ትደሰታለች።

፳፮ እንግዲህ እነሆ ይህ የያዕቆብ ቋንቋ ነበር።

፳፯ እናም እንግዲህ የዮሴፍ ዘር ቅሪት የሆኑት፣ እንደልብሱ የጠፉት፣ ከእኛ የተገነጠሉ መሆናቸውንስ ማን ያውቃል? አዎን፣ እናም በክርስቶስ እምነት ፈጥነን ካልቆምን እኛም እራሳችን እንዲሁ እን ሆናለን።

፳፰ እናም አሁን እንዲህ ሆነ ሞሮኒ ይህ ንን በተናገረ ጊዜ ወደ ፊት ሄደ፤ እናም ደግሞ ተቃውሞ ባለበት ምድር ሁሉ መል ዕክተኞን ላከና፣ አማሊቅያንና የተገነጠሉት አማሊቅያውያን ተብለው በሚጠሩት ላይ ይነሱባቸው ዘንድ ነፃነታቸውን ለመጠበቅ የሚፈልጉትን ሰዎች በሙሉ በአንድ ላይ እንዲሰበሰቡ አደረገ።

፳፱ እናም እንዲህ ሆነ የሞሮኒ ሰዎች ከአ ማሊቅያውያን በቁጥር ብዙ መሆናቸውን አማሊቅያ በተመለከተ ጊዜ፣ እናም ደግሞ ህዝቡ ስላደረጓቸው ጉዳዮች ፍትህነት በተ መለከተ ጥርጣሬአቸውን ተመለከተ፣ ስለ ዚህ ዓላማውም አይሳካልኝም ብሎ በመፍ ራት ፈቃደኛ የሆኑትን ሰዎች ወሰደና፣ ወደ ኔፊ ምድር ሸሸ።

፴ እንግዲህ ሞሮኒም ከእንግዲህ ላማና ውያን ከዚህ የበለጠ ብርታት ሊኖራቸው አይገባም ብሎ አሰበ፤ ስለዚህ የአምሊኪ ውያን ሰዎችን ለማቋረጥ፣ ወይም እነርሱን ለመውሰድና፣ ለመመለስ፣ እናም አማሊቅ ያን ለመግደል አሰበ፤ አዎን፣ ላማናውያንን በቁጣ በእነርሱ ላይ እንደሚያነሳሳና ከእነ ርሱ ጋር ለውጊያ እንዲመጡ እንደሚያ ደርግ አውቋልና፤ እናም አማሊቅያ አላ ማውን ለማግኘት እንዲህ እንደሚያደርግ ያውቅ ነበር።

፴፩ ስለዚህ ሞሮኒ በአንድ ላይ የሰበሰባ ቸውንና፣ ያስታጠቃቸውን፣ እናም ሰላ ምን ለመጠበቅ ቃል እንዲገቡ ያደረጋቸ ውን ወታደሮች መውሰድ አስፈላጊ ነው በማለት አሰበ፤ እናም እንዲህ ሆነ ወታደ ሮቹን ወሰደ፣ እናም በምድረበዳው ውስጥ የአማሊቅያን መንገድ ለመስበር ድንኳና ቸውን በመያዝ ወደ ምድረበዳው ተንቀ ሳቀሱ።

፴፪ እናም እንዲህ ሆነ እንደ ፍላጎቱም አደረገና፣ ወደ ምድረበዳው ዘመተ፣ እናም የአማሊቅያን ሠራዊት እርምጃ አቋረጠ።

፴፫ እናም እንዲህ ሆነ አማሊቅያ ትንሽ ቁጥር ካላቸው ሰዎች ጋር ሸሸና፣ ቀሪዎቹ በሞሮኒ እጅ ገቡ፣ እናም ወደ ዛራሔምላ ምድር ተመልሰው ተወሰዱ።

፴፬ እንግዲህ፣ ሞሮኒ በዋናው ዳኛ ᐸየተ ሾመ፣ እናም በህዝቡ ድምፅ የተመረጠ ሰው በመሆኑ፣ ስለዚህ በኔፋውያን ሠራ ዊት መካከል በእነርሱ ላይ ስልጣኑን ለመ ጀመርና ለመመስረትና እንደፈቃዱ ስል ጣን በእነርሱ ላይ ነበረው።

፴፭ እናም እንዲህ ሆነ ነፃ መንግስት ያስ ተዳድሩበት ዘንድ፣ የነፃነቱን መንስኤ ለመ ርዳት ወደ ቃል ኪዳኑ ያልገቡትን አማሊቅ ያውያን እንዲገደሉ አደረገ፤ እናም የነፃነ ቱን ቃል ኪዳን ክደው የነበሩት ጥቂት ብቻ ነበሩ።

፴፮ እናም ደግሞ እንዲህ ሆነ፣ ሞሮኒ በኔፋውያን በተያዙ ቦታ በምድሪቱ ሁሉ ባሉት ሰገነት ላይ የነፃነት ዓርማው እንዲሰ ቀል አደረገ፤ እናም ሞሮኒ የነፃነት ባንዲራን በኔፋውያን መካከል እንደዚህ ተከለው።

፴፯ እናም በድጋሚ በምድራቸው ላይ ሰላምን ማግኘት ጀመሩ፣ እናም እስከ አስራ ዘጠነኛው የመሣፍንት አገዛዝ መጨ ረሻ መቃረቢያ ድረስ ምድሪቱ በሰላም ተዳ ደረች።

፴፰ እናም ሔለማንና ᐸሊቀ ካህናቱም ደግሞ በቤተክርስቲያኗ ስርዓትን አስከ በሩ፤ አዎን ለአራት ዓመታት ያህል እን

ኳን ሰላም በዝቶላቸው እናም በቤተክርስ ቲያኗም ተደስተው ነበር።

፴፱ እናም እንዲህ ሆነ በፅናት ነፍሳቸው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚድን [ሀ]እያ መኑ የሞቱም ብዙዎች ነበሩ፤ ስለዚህ ከዓ ለምም የወጡት በደስታ ነበር።

፵ እናም በዓመቱ በአንዳንድ ወቅት ውስ ጥም በምድሪቱ ተደጋጋሚ በነበረው ንዳድ ጥቂቶች ሞቱ—ነገር ግን ሰዎች በተፈጥ ሮው የአየር ፀባይ ቢገደዱም እግዚአብሔር የበሽታውን መንስኤ ለማስወገድ መልካም [ሀ]ተክሎችን እና ስሮችን በማዘጋጀቱ ብዙ ዎች በንዳዱ አልሞቱም—

፵፩ ነገር ግን ብዙዎች በእርጅናቸው ሞተ ዋል፤ እናም እኛ መገመት እንዳለብን ክር ስቶስን በማመን የሞቱት በእርሱ [ሀ]ደስተ ኞች ናቸው።

ምዕራፍ ፵፯

አማሊቅያ የላማናውያን ንጉስ ለመሆን ክህደትን፣ ግድያን፣ እናም ሴራን ተጠ ቀመ—ከኔፋውያን የተገነጠሉት ከላማና ውያን የበለጡ ክፉዎች እና አስፈሪዎች ናቸው። በ፸፪ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እንግዲህ እኛም በምዝገባችን ወደ አማሊቅያና ከእርሱ ጋር ወደ ምድረበዳው [ሀ]ስለሸሹት እንመለስ፤ እነሆም፣ ከእርሱ ጋር የሄዱትን ይዞ ሄደ፣ እናም ወደ [ለ]ኔፊ ምድር በላማናውያን መካከል ሄደ፣ እናም የላማናውያን ንጉስ ከኔፋውያን ጋር በድ ጋሚ እንዲዋጉ እራሳቸውን በአንድ ላይ እንዲሰበስቡ አዋጁን በምድሪቱ ላይ እስ ከሚልክ ድረስ ላማናውያንን በኔፊ ህዝብ ላይ ለቁጣ እንዲነሳሱ አደረገ።

፪ እናም እንዲህ ሆነ አዋጁ በእነርሱ መካ ከል በደረሰ ጊዜ እጅግ ፈርተው ነበር፤ አዎን፣ ንጉሱን ለማስቀየምም ፈርተው ነበር፤ እናም ደግሞ ህይወታችንን እናጣለን በማለት ስለፈሩም ከኔፋውያን ጋር መዋጋ ትን አልደፈሩም። እናም እንዲህ ሆነ አል ተቀበሉም ነበር፣ ወይም ከእነርሱም አብ ዛኛዎቹ የንጉሱን ትዕዛዛት አልተቀበሉም።

፫ እናም አሁን እንዲህ ሆነ ንጉሱ ታዛዥ ባለመሆናቸው ተቆጥቶ ነበር፤ ስለዚህ ለትዕዛዛቱ ታዛዥ የሆኑትን ሠራዊት መሪ ነትን ለአማሊቅያ ሰጠ፤ እናም እንዲሄድና የጦር መሳሪያዎቻቸውን እንዲይዙ እንዲ ያስገድዳቸው አዘዘው።

፬ እናም እነሆ ይህ የአማሊቅያ ፍላጎት ነበር፣ ክፉ ነገርን ለማድረግ የረቀቀ ሰው ነበር፣ ስለዚህ የላማናውያን ንጉስን ከዙ ፋኑ ለማውረድ በልቡ አቀደ።

፭ እናም አሁን ንጉሱን በሚወዱት ላማና ውያን ክፍል ተቀባይነትን አገኘ፤ እናም ታዛዥ ባልሆኑትም ዘንድ ተቀባይነትን ለማ ግኘት ፈለገ፤ ስለዚህ [ሀ]ኦኒዳ ተብሎ ወደሚ ጠራው ስፍራም ሄደ፤ ምክንያቱም ላማና ውያን በሙሉ ወደዚያ ስፍራ ሸሽተው ነበ ርና፤ ወታደሮቹ መምጣታቸውን በማወ ቃቸው፣ እናም እነርሱን እንደሚያጠፉአ ቸው ስለገመቱ የጦር መሳሪያዎቹ ወዳሉ በት ስፍራ፣ ወደ ኦኒዳ ሸሹ።

፮ እናም ከኔፋውያን ጋር ለመዋጋት እን ደማይገደዱ ቁርጥ ውሳኔን በአዕምሮአቸው ስለቀረፁ አንድን ሰው በራሳቸው ላይ ንጉሳ ቸው እናም መሪያቸው አድርገው ሾሙ።

፯ እናም እንዲህ ሆነ ለጦርነቱ ለመዘጋጀት አንቲጳስ ተብሎ በሚጠራው ተራራ ጫፍ እራሳቸውን በአንድ ላይ ሰበሰቡ።

፰ እንግዲህ እንደንጉሱ ትዕዛዝ መሰረት ከእነርሱ ጋር ለመዋጋት የአማሊቅያ አስተ ሳሰብ አልነበረም፣ ነገር ግን እነሆ፣ እራሱን የበላይ በማድረግ ያስቀምጥ ዘንድ፣ እናም ንጉሱንም ከዙፋኑ ያወርደው ዘንድ እናም መንግስቱንም ይወስድ ዘንድ በላማናውያን ወታደሮች መወደድ የእርሱ ፍላጎት ነበር።

፱ እናም እነሆ፣ የእርሱም ሠራዊት በአን

፴፱ሀ ሞሮኒ ፯፥፫፣ ፵፩።
፵ሀ ት. እና ቃ. ፷፫፥፵፱።
፵፩ሀ ራዕ. ፲፬፥፲፫።

፵፯ ፩ሀ አልማ ፵፮፥፴፫።
ለ ፪ ኔፊ ፭፥፩–፳፬፤
አምኒ ፩፥፲፪–፲፫።

፭ሀ አልማ ፴፪፥፬።

ቲጳስ ተራራ አጠገብ ባለው ሸለቆ ድንኳን
እንዲጥሉ አደረገ።
፲ እናም እንዲህ ሆነ ምሽት በሆነም ጊዜ
ወደ አንቲጳስ ተራራ ስሙም ሌሆንቲ ወደ
ተባለው መሪያቸው ከእርሱ ጋር መነጋ
ገር በመፈለጉ ወደ ተራራው ግርጌ ይመጣ
ዘንድ በሚስጥር መልዕክተኛ ላከ።
፲፩ እናም እንዲህ ሆነ ሌሆንቲ መልዕ
ክቱን በተቀበለ ጊዜ ወደ ተራራው ግርጌ
መሄድ አልደፈረም ነበር። እናም እንዲህ
ሆነ አማሊቅያ እንዲመጣለት ስለፈለገ ለሁ
ለተኛ ጊዜ መልዕክተኛ ላከ። እናም እንዲህ
ሆነ ሌሆንቲ ግን አልመጣለትም፤ እናም
በድጋሚ ለሶስተኛ ጊዜ መልዕክተኛ ላከ።
፲፪ እናም እንዲህ ሆነ አማሊቅያ ሌሆንቲን
ከተራራው ለማስወረድ አለመቻሉን ባወቀ
ጊዜ፣ ወደ ሌሆንቲ የጦር ሰፈር በመጠጋት
ወደ ተራራው ሄደ፤ እናም እንዲመጣ በመ
ፈለጉ ሌሆንቲ ጠባቂዎቹን ከእርሱ ጋር ይዞ
እንዲመጣ በድጋሚ ለአራተኛ ጊዜ መል
ዕክተኛን ላከ።
፲፫ እናም እንዲህ ሆነ ሌሆንቲ ከጠባቂዎቹ
ጋር ወደ አማሊቅያ በመጣ ጊዜ፣ ሌሆንቲ
አማሊቅያን በሠራዊቱ ላይ ሁለተኛ መሪ
የሚያደርገው ከሆነ፣ ከወታደሮቹ ጋር በም
ሽት ጊዜ እንዲመጣና፣ በጦር ሰፈራቸው
ያሉትን ንጉሱ ትዕዛዝ የሰጣቸውን ሰዎች
እንዲከቡአቸው፣ እናም እነርሱንም በሌሆ
ንቲን እጅ አሳልፎ ሊሰጣቸው ፈልጎ ነበር።
፲፬ እናም እንዲህ ሆነ ሌሆንቲ ከራሱ
ሰዎች ጋር መጣና፣ የአማሊቅያን ሰዎች
ከበቡአቸው፣ ስለዚህ ሌሊቱ ነግቶ ከመን
ቃታቸው በፊት በሌሆንቲ ወታደሮች ተከ
በው ነበር።
፲፭ እናም እንዲህ ሆነ መከበባቸውን
በተመለከቱ ጊዜ እንዳይጠፉ ከወንድሞ
ቻቸው ጋር እንዲቀላቀሉ ይፈቅድላቸው
ዘንድ አማሊቅያን ለመኑት። እናም ይህ
አማሊቅያ የሚፈልገው ነገር ነበር።
፲፮ እናም እንዲህ ሆነ የራሱን ሰዎች ከን
ጉሱ ትዕዛዝ [ሀ]ተቃራኒ በሆነ ሁኔታ አሳልፎ
ሰጣቸው። እናም ንጉሱን ከዙፋኑ ለማው
ረድ ያቀደው ይፈፀም ዘንድ አማሊቅያ የፈ
ለገው ይህንን ነበር።
፲፯ እንግዲህ ዋናው መሪያቸው ከተገደለ
ሁለተኛውን ዋና መሪ አድርጎ መሾም በላ
ማናውያን መካከል የነበረ ልምድ ነበር።
፲፰ እናም እንዲህ ሆነ አማሊቅያ ከአገል
ጋዮቹ አንዱ፣ ሌሆንቲ እንዲሞት ቀስ በቀስ
መርዝ እንዲሰጠው አደረገ።
፲፱ እንግዲህ፣ ሌሆንቲ በሞተ ጊዜ፣
ላማናውያን አማሊቅያን መሪያቸው፣ እናም
ዋና አዛዣቸው አድርገው ሾሙት።
፳ እናም እንዲህ ሆነ አማሊቅያ ከወታደ
ሮቹ ጋር (ፍላጎቱ ስለተፈፀመለት) ወደ ኔፊ
ምድር፣ ወደ ኔፊ ከተማ፣ ዋና ከተማ ወደ
ሆነችው ተንቀሳቀሰ።
፳፩ እናም ንጉሱ አማሊቅያ ትዕዛዙን ፈፅ
ሟልና አማሊቅያ በርካታ ሠራዊቶቹ ከኔፋ
ውያን ጋር ለመዋጋት እንዲሄዱ በአንድ ላይ
ሰብስቧቸዋል ብሎ በመገመቱ ከጠባቂዎቹ
ጋር እርሱን ለመገናኘት ሄደ።
፳፪ ነገር ግን እነሆ፣ ንጉሱ እርሱን ለማ
ግኘት በሄደ ጊዜ፣ አማሊቅያ አገልጋዮቹ
ንጉሱን እንዲያገኙት እንዲሄዱ አደረገ።
እናም እነርሱ ሄዱና፣ በንጉሱ ፊት በታላ
ቅነቱ ያከበሩት ለመምሰል ሰገዱለት።
፳፫ እናም እንዲህ ሆነ ንጉሱ ከኔፋውያን
በወሰዱት ወግ ለሠላም ተምሣሌት እንደ
ሆነው እንደላማናውያን ወግ እነርሱን ለማ
ንሳት እጁን ዘረጋ።
፳፬ እናም እንዲህ ሆነ ንጉሱ የመጀመሪ
ያውን ከመሬት ባነሳው ጊዜ፣ እነሆ ንጉሱን
በልቡ ላይ ወጋው፤ እናም እርሱም በመ
ሬት ላይ ወደቀ።
፳፭ እንግዲህ የንጉሱ አገልጋዮች ሸሹ፣
እናም የአማሊቅያ አገልጋዮች እንዲህ ሲሉ
ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ጮኹ፥
፳፮ እነሆ፣ የንጉሱ አገልጋዮች ልቡን
ወጉት፣ እናም እርሱ ወደቀ፣ እነርሱም
ሸሹ፤ እነሆ፣ ኑና ተመልከቱ።
፳፯ እናም እንዲህ ሆነ አማሊቅያ ወታደ

[ሀ] አልማ ፴፯፡ ፲።

ሮቹ ወደ ፊት እንዲጓዙና፣ ንጉሱ ምን እን ደሆነ እንዲመለከቱ አዘዘ፤ እናም ወደ ስፍ ራው በመጡበት ጊዜ ንጉሱ ደምቶ ከመሬት ላይ ወድቆ ሲያገኙት፣ አማሊቅያ የተቆጣ አስመስሎ እንዲህ አለ፡ ንጉሱን የሚወድ ቢኖር፣ እንዲሄድ ይደረግና፣ የንጉሱንም አገልጋዮች አሳዶ ይግደላቸው።

፳፰ እናም እንዲህ ሆነ ንጉሱን የሚወ ዱት በሙሉ፣ ይህንን ቃላት በሰሙ ጊዜ መጡ፣ እናም የንጉሱን አገልጋዮች ተከ ታተሉአቸው።

፳፱ እናም የንጉሱ አገልጋዮች ወታደ ሮቹ እንደተከታተሉአቸው በተመለከቱ ጊዜ በድጋሚ ፈርተው ነበር፣ እናም ወደ ምድረበዳው ሸሹና፣ ወደ ዛራሔምላ ምድር መጡና፣ ᵐከአሞን ህዝብ ጋር ተቀላቀሉ።

፴ እናም የተከታተሉአቸው ወታደሮች በከንቱ ሁኔታ ከተከተሉአቸው በኋላ ተመ ለሱ፤ እናም አማሊቅያ እንደዚህ በማጭበ ርበር የህዝቡን ልብ አገኘ።

፴፩ እናም እንዲህ ሆነ በሚቀጥለው ቀንም ከሠራዊቱ ጋር ወደ ኔፊ ከተማ ገባ፣ እናም ከተማዋንም ተቆጣጠረ።

፴፪ እናም እንግዲህ እንዲህ ሆነ ንግስቲቱ ንጉሱ መገደሉን በሰማች ጊዜ—አማሊቅያ ለንግስቲቱ ንጉሱ በአገልጋዮቹ መገደሉን፣ እርሱም ከወታደሮቹ ጋር እንደተከተላቸው ነገር ግን ከንቱ እንደነበር፣ እናም እንዳመለ ጡአቸው መልዕክተኛ በመላክ አሳወቃት—

፴፫ ስለዚህ፣ ንግስቲቱ ይህንን መልዕክት በተቀበለች ጊዜ አማሊቅያ የከተማዋን ነዋ ሪዎች ህይወት እንዲያተርፍ እንደምትፈ ልግ ላከችበት፤ እናም ደግሞ እርሱ ወደ እርሷ እንዲመጣ ፈለገች፤ እናም ደግሞ የንጉሱን መሞት በተመለከተ ምስክሮችን ለመረጃ እንዲያመጣላት ፈለገች።

፴፬ እናም እንዲህ ሆነ አማሊቅያ ንጉሱን የገደለውንና፣ ከእርሱ ጋር የነበሩትን አገ ልጋዮች በሙሉ ወሰደና፣ ንግስቲቱ በተ ቀመጠችበት ስፍራ ሄዱ፤ እናም የንጉሱ በራሱ አገልጋዮች መገደሉን ሁሉም መሰ ከሩላት፤ እናም ደግሞ እንዲህ አሉ፡ እነ ርሱም ሸሽተዋል፤ ይህ እራሱ በእነርሱ ላይ ምስክር አይሆንምን? የንጉሱን ሞት በተመ ለከተም እንደዚህ ንግስቲቱን አሳመኗት።

፴፭ እናም እንዲህ ሆነ አማሊቅያ የንግስ ቲቱን ድጋፍ ፈለገ፤ እናም አገባትና፣ በማ ጭበርበሩና፣ በብልጥ አገልጋዮቹ እርዳታ ግዛቱን እንደዚህ አገኘ፤ አዎን፣ በምድ ሪቱ ላይ ሁሉ ᵐባሉ በላማናውያንና፣ በል ሙኤላውያን፣ እናም በእስማኤላውያንና፣ ከኔፊ ንግስና እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ከኔ ፋውያን በተገነጠሉት ሁሉ መካከል ንጉስ መሆኑ ታወቀ።

፴፮ እንግዲህ እነዚህ ᵐተገንጣዮች ከኔ ፋውያን አንድ ዓይነት ትምህርት እና መረጃ ነበራቸው፤ አዎን በዚሁ ዓይነት ሁኔታ ᵃስለጌታ እውቀት ተምረው ነበር፤ ይሁን እንጂ ከመገንጠላቸው ብዙም ሳይ ቆይ፣ እንደ ላማናዊያን ባህል በመጠጣት፣ ለስንፍና፣ እናም ለሁሉም አይነትዝሙት ነት ቦታ በመስጠት፣ አዎን፣ ጌታ አምላካ ቸውን ሙሉ በሙሉ ረሱት፣ ከላማናውያን የበለጠ ጠጣርና፣ ᵃንስሃን የማይገቡ ስለመ ሆናቸው፤ እናም ኃጢአተኞችና፣ አስፈ ሪዎች ስለመሆናቸው ለመተረክ የሚያስ ገርም ነበር።

ምዕራፍ ፵፯

አማሊቅያ ላማናውያንን በኔፋውያን ላይ አነሳሳ—ሞሮኒ የክርስቲያን ጉዳዮችን እን ዲከላከሉ ህዝቡን አዘጋጀ—እርሱም በመ ብትና በነፃነት ተደሰተ እናም የእግዚአብ ሔር ኃያል ሰው ነው። በ፳፪ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ አማሊቅያ ግዛ ቱን እንዳገኘ የላማናውያንን የልብ ስሜት በኔፊ ህዝብ ላይ እንዲነሳሱ ቀሰቀሰ፤ አዎን፣

፳፱ ᵐ አልማ ፴፫፡ ፲፩–፲፪። ᵃ ቅ.መ.መ. አንቲ-ኔፊ-ሌሂ።
፴፩ ᵐ ያዕቆ. ፩፡ ፲፫–፲፡ ᵃ ᵐ ቅ.መ.መ. ክህደት።
ᵃ ዕብ. ፲፡ ፳፯–፳፱፣ አልማ ፳፱፡ ፴።
ᵃ ᵐ ሐ ኤር. ፳፡ ፲፪።

ሰዎች ኔፋውያንን በመቃወም ከሰገነታቸው ላይ በመሆን ለላማናውያን እንዲናገሩ ሾማ ቸው።

፪ እናም ወደ መሣፍንቱ የአስራ ዘጠነኛው የንግስ ዘመን መጨረሻ ላይ አማሊቅያ ልባ ቸው በኔፋውያን ላይ እንዲነሳሳ አደረገ፤ ዕቅዱን እስከዚህ ድረስ በመፈፀሙ፤ አዎን በላማናውያን ላይ ንጉስ ለመሆን እንደፈለ ገው በመደረጉ፣ በምድሪቱ ላይም ደግሞ፤ አዎን፣ እናም በኔፋውያንም ሆነ በላማናው ያን ምድር ባሉት ሰዎች ሁሉ ላይ እንዲነ ግስ ፈለገ።

፫ ስለዚህ የላማናውያንን ልብ በማጠ ጠሩ፣ እናም አዕምሮአቸው እንዲታወር በማድረጉ፣ እናም ለቁጣ እነርሱን በማነ ሳሳቱ፣ ብዙ ወታደሮች ኔፋውያንን ለመ ዋጋት በአንድ ላይ እራሳቸውን እስከሚሰ በስቡ ድረስ ዕቅዱን ፈፀመ።

፬ እርሱም ኔፋውያንን ለመግዛት፣ እናም እነርሱን ወደ ባርነት ለማምጣት የሰዎቹ ቁጥር ታላቅ በመሆኑ ታላቅ ውሳኔን አድ ርጎ ነበር።

፭ እናም የኔፋውያንን ብርታትና፣ የመ ጠለያ ቦታዎቻቸውን፣ እናም ደካማ የሆነ ውን የከተማቸውን ክፍል የሚያውቁ በመ ሆናቸው ዞራማውያንን *ዋና ሻምበል በማ ድረግ ሾሞ ነበር፤ ስለዚህ እነርሱን በሠ ራዊቱ ላይ ዋና ሻምበል በማድረግ ሾመ።

፮ እናም እንዲህ ሆነ የጦር ሰፈራቸ ውን አነሱና፣ በምድረበዳው ውስጥ ወደ ዛራሔምላ ምድር ሄዱ።

፯ እንግዲህ እንዲህ ሆነ አማሊቅያ ስልጣ ንን በማምታታት፣ እና በማጭበርበር እያ ገኘ ባለበት ጊዜ፣ ሞሮኒ፣ በሌላ በኩል የሰ ዎችን አዕምሮ ለጌታ ለአምላካቸው ታማኝ እንዲሆኑ *ያዘጋጅ ነበር።

፰ አዎን፣ የኔፋውያን ወታደሮችን አጠ ናከረ፣ እናም ትናንሽ ምሽጎችን፣ ወይ ንም የመጠለያ ስፍራዎችን እንዲሰሩ አደ ረገ፤ ወታደሮቹን ለመክበብ መሬቱ እን ዲቆለል፣ እናም ደግሞ በድንጋይ ግድ ግዳም ዙሪያውን፣ ከተሞቻቸውንና የም ድሪቱን ዳርቻ፣ አዎን፣ በምድሪቱ ዙሪያ ሁሉ ከበበ።

፱ እናም በደንብ ባልተዘጋጀው ምሽጋ ቸው ብዙ ቁጥር ያላቸውን ሰዎች አስቀ ምጦ ነበር፤ እናም በኔፋውያን የተያዙትን ምድር እንደዚህ አጠረና አጠናከረ።

፲ እናም በጌታ ይኖሩ ዘንድ፣ እናም በጠላ ቶቻቸው የክርስቲያኖች ጉዳይ ተብሎ የተ ጠራውን ይጠብቁ ዘንድ፣ ነፃነታቸውን፣ ምድራቸውን፣ ሚስቶቻቸውን፣ ልጆቻ ቸውንና ሰላማቸውን *ለመደገፍ ተዘጋ ጅቶ ነበር።

፲፩ እናም ሞሮኒ ጠንካራና፣ ኃያል ሰው ነበር፤ እርሱም ፍፁም የሆነ *ዕውቀት ያለው ሰው ነበር፤ አዎን በደም መፋሰስ የማይደ ሰት ሰው ነበር፤ ነፍሱም በሀገሩመብትና ነጻ ነት፣ እናም በወንድሞቹ ከመታሰርና ከባር ነት መብትና ነጻነት ትደሰታለች፤

፲፪ አዎን፣ እግዚአብሔር በህዝቡ ላይ ብዛት ያላቸው ልዩ መብቶችን፣ እናም በረከቶችን በማድረጉ ለአምላክ ምስጋናን በማቅረብ ልቡ የተሞላ፤ ለህዝቡ *ደህንነት እናም ጥበቃ ሲል እጅግ የሰራ ሰው ነው።

፲፫ አዎን፣ እናም እርሱ በክርስቶስ ፅኑ እምነት ያለው ሰው ነበር፤ እናም የህዝ ቡን መብት፣ ሀገሩንና ኃይማኖቱን፣ ደሙ እስከሚፈስ ድረስ እንኳን ለመጠበቅ መሃላ *ምሎ ነበር።

፲፬ እንግዲህ አስፈላጊ ከሆነ ኔፋውያን ደማቸው እስከሚፈስም ድረስ እንኳን ከጠላቶቻቸው እራሳቸውን እንዲከላከሉ ተምረዋል፤ አዎን፣ እናም ደግሞ ህይወ ታቸውን ከመጠበቅ በቀር *በጭራሽ እንዳ ያጠቁ፣ አዎን፣ እናም በጠላቶቻቸው ላይ

፴፯ ፭ *ሀ አልማ ፴፫፡፲፤
፯ *ሀ አልማ ፴፱፡፳፡
፲ *ሀ አልማ ፴፯፡፲፪–፲፫፡
፲፩ *ሀ ቅ.መ.መ. ማስተዋል።
፲፪ *ሀ ቅ.መ.መ. በጎ ድርጊት።
፲፫ *ሀ አልማ ፴፯፡፳–፳፪።
፲፬ *ሀ አልማ ፴፫፡፴–፴፯፤
ዮ ኔፊ ፫፡፳–፳፩፤
ሞር. ፫፡፲–፲፩፤
ት.እና ቃ. ፣፳፡፡፲፯።

ካልሆነ በቀር ጎራዴያቸውን እንዳያነሱ፣ ተምረዋል።

፲፭ እናም ይህ እምነታቸው ነበር፣ ይህ ንንም በማድረግ እግዚአብሔር በምድሪቱ ላይ ያበለፀጋቸዋል፣ ወይንም በሌላ አነጋገር የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት በመጠበቅ ታማኞች እስከሆኑ ድረስ በምድሪቱ ላይ ያበለፀጋቸዋል፤ አዎን፣ እንዲሸሹ፣ አለበለዚያም በሚመጣባቸው አደጋ መሰረት ለጦርነት እንዲዘጋጁ ያስጠነቅቃቸዋል፤

፲፮ እናም ደግሞ፣ እግዚአብሔርም ከጠላቶቻቸው ለመከላከል ወዴት እንደሚሄዱ እንዲያውቁ ያደርጋቸዋል፣ ይህንንም በማድረግ፣ ጌታ ያድናቸዋል፤ ይህም የሞሮኒ እምነት ነበር፣ እናም "በደም መፋሰስ ሳይሆን በመልካም ስራ ሕዝቡን ለመጠበቅ፤ አዎን፣ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት በመጠበቅ፣ አዎን፣ እናም ክፋትን በመቋቋም ልቡም በዚያ ተመካች።

፲፯ አዎን፣ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፤ ሰዎች ሁሉ እንደ ሞሮኒ ከሆኑና ከነበሩ፣ እናም የሚሆኑ ከሆነ፣ እነሆ፣ የሲኦል ኃይል እራሱ ለዘለዓለም ይናወጥ ነበር፤ አዎን፣ "ዲያብሎስም በሰው ልጆች ልብ ላይ ስልጣን በጭራሽ ባልኖረውም ነበር።

፲፰ እነሆ እርሱም የሞዛያ ልጅ እንደነበረው እንደ አሞን ዓይነት ነበር፤ አዎን፣ እናም እንደሌሎቹ የሞዛያ ልጆች ነበር፤ አዎን፣ እናም ደግሞ የእግዚአብሔር ሰዎች እንደነበሩት እንደ አልማና ልጆቹ ነበር።

፲፱ እናም እነሆ፣ ሔለማንና ወንድሞቹ ለህዝቡ ከሞሮኒ ያነሰን አገልግሎት የሰጡ አልነበሩም፤ ምክንያቱም እነርሱ የእግዚአብሔርን ቃል ሰብከዋል፣ እናም ቃላቸውን የሰሙአቸውን ሰዎች በሙሉ ለንስሃ አጥምቀዋቸዋል።

፳ እናም እነርሱ ሄዱና፣ ህዝቡ በቃላቸው የተነሳ በጌታ "የተመረጡ እስከሚሆኑ ድረስ እራሳቸውን ^ዝቅ አደረጉ፣ እናም አዎን ለአራት ዓመታትም ያህል በራሳቸው መካከል ከጦርነትና ከፀብ ነፃ ሆኑ።

፳፩ ነገር ግን፣ እንደተናገርኩት፣ በአስራ ዘጠነኛው ዓመት መጨረሻ፣ አዎን፣ በመካከላቸው ሰላም ቢሆንም እንኳን፣ ሳይፈልጉ ከወንድሞቻቸው ከላማናውያን ጋር እንዲጣሉ ተገደዱ።

፳፪ አዎን፣ እናም በአጠቃላይ ፈቃደኞች ባይሆኑም እንኳን፣ ከላማናውያን ጋር ለብዙ ዓመታት ጦርነትን በጭራሽ አላቆሙም ነበር።

፳፫ እንግዲህ በደም መፋሰሱ ደስተኞች ባለመሆናቸው በላማናውያን ላይ ጦርነት በማስነሳታቸው "አዝነው ነበር፤ አዎን፣ እናም ይህ ብቻም አልነበረም—ብዙ ወንድሞቻቸውንም ከዚህ ዓለም ወደ ዘለአለማዊው ዓለም ከአምላካቸው ጋር ለመገናኘት ሳይዘጋጁ እንዲላኩ መንስኤ በመሆናቸው አዝነው ነበር።

፳፬ ይሁን እንጂ፣ በአንድ ወቅት ወንድሞቻቸው በነበሩት፣ አዎን፣ እናም ከቤተክርስቲያናቸው "በተገነጠሉትና፣ ትተዋቸው በሄዱት፣ እናም ከላማናውያን ጋር በመሆን ሊያጠፋቸው በሄዱት አረመኔ ሰዎች ጭካኔ ^ሚሰቶቻቸውና፣ ልጆቻቸው እንዲጨፈጨፉና እንዲያጠፏቸው ዘንድ ህይወታቸውን ለመስጠት ለመፍቀድ አልቻሉም።

፳፭ አዎን፣ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት የጠበቀ እስካለ ድረስ ወንድሞቻቸው በኔፋውያን ደም ደስታን እንዲያገኙ ለመመልከት አይቻላቸውም፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን እንደነበረው፣ ትዕዛዛቱን ከጠበቁ በምድሪቱ ላይ ይበለፀጋሉ።

ምዕራፍ ፵፱

ወራሪ ላማናውያን የአምኒሀንና የኖህን የምሽግ ከተማዎች ለመያዝ አልቻሉም—አማሊቅያ እግዚአብሔርን ረገመ፣ እናም

፲፯ ሀ አልማ ፶፭፡፲፱።
፲፯ ሀ ፩ ኔፊ ፳፪፡፳፯፤ ፪ ኔፊ ፭፡፲፫።
፲ ኔፊ ፮፡፲፭።
፳ ሀ ፩ ኔፊ ፲፯፡፴፭።
ለ ቅ.መ.መ. ትሁት፣ ትሕትና።
፳፫ ሀ ት.እና ቃ. ፵፪፡፴፭።
፳፬ ሀ ቅ.መ.መ. ክህደት።
ለ አልማ ፴፯፡፲፪።

*የሞሮኒን ደም ለመጠጣት ማለ—ሔለማ
ንና ወንድሞቹ ቤተክርስቲያኗን ማጠናከር
ቀጠሉ። በ፸፪ ም.ዓ. ገደማ።*

፩ እናም አሁን እንዲህ ሆነ በአስራ ዘጠ
ነኛው ዓመት አስራ አንደኛ ወር፣ በወሩ
አስረኛ ቀን፣ የላማናውያን ወታደሮች ወደ
አሞኒሀ ምድር እንደቀረቡ ታዩ።
፪ እናም እነሆ፣ ከተማዋ በድጋሚ ተገን
ብታ ነበር፣ ሞሮኒም በከተማዋ ዳርቻ ሠራ
ዊቱን አስፍሯል፣ እናም በዙሪያቸው ከላ
ማናውያን ጦርና ድንጋይ የሚጋርዳቸውን
አፈር ቆልለዋል፤ እነሆም፣ በድንጋይና
በጦር ይዋጉ ነበርና።
፫ እነሆ ሀየአሞኒሀ ከተማ ድጋሚ ተሰርታ
ነበር ብያለሁ። እንዲህ እላችኋለሁ፤ አዎን፣
ግማሹ ክፍል በድጋሚ ተሰርቶ ነበር፤ እናም
ላማናውያን ከህዝቡ ክፋት የተነሳ አንዴ
አጥፍተውት ስለነበር በድጋሚ በቀላሉ
የሚያዝ ነው በማለት ገምተው ነበር።
፬ ነገር ግን እነሆ፣ ቁጣቸው ምን ያህል
ታላቅ ነበር፤ እነሆም፣ ኔፋውያን በዙሪ
ያቸው ያለውን ተረተር ቆፍረው ቆለሉ፣
ይህም ትልቅ በመሆኑ ላማናውያን በዚህ
ላይ ጥቃትን ይፈፅሙ ዘንድ ድንጋይ እናም
ጦር ለመወርወር አልቻሉም፣ መግቢያቸው
በኩል ካልሆነም በቀር በእነርሱ ላይ ለመ
ምጣትም አልቻሉም ነበር።
፭ እንግዲህ በዚህ ጊዜ የላማናውያን ዋና
ሻምበል፣ ኔፋውያን የስፍራቸውን ደህንነት
ለማዘጋጀት ባደረጉት ጥበብ እጅግ ተደ
ንቆ ነበር።
፮ እንግዲህ የላማናውያን መሪዎች በቁ
ጥር ብዙ በመሆናቸው፣ አዎን ከዚህ ቀደም
እንዳደረጉት በእነርሱ ላይ ለመምጣት እድ
ሉን ለመጠቀም እንችላለን ብለው ገምተው
ነበር፤ አዎን፣ እናም ደግሞ በጋሻዎችና፣
በደረት ኪሶቻቸው እራሳቸውን አዘጋጅ
ተው ነበር፤ እናም ደግሞ ከቆዳ በተሰሩ
ልብሶች፣ አዎን፣ እርቃናቸውን በሚ
ሸፍኑላቸው ወፍራም ልብሶች፣ እራሳቸ
ውን አዘጋጅተው ነበር።
፯ እናም እንደዚህ በመዘጋጀታቸውም
በቀላሉ ወንድሞቻቸውን እንደሚያሸ
ንፉና በባርነት ቀንበር ስር እንደሚያደ
ርጉ፣ ወይም እንደፍላጎታቸውም እንደ
ሚገድሉአቸውና እንደሚጨፈጭፉቸው
ገምተዋል።
፰ ነገር ግን እነሆ፣ በከፍተኛ ሁኔታ እስ
ከሚገርማቸው ድረስ በሌሂ ልጆች መካ
ከል ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ሀተዘጋጅ
ተው ነበር። እንግዲህ በሞሮኒ ትዕዛዝም
መሰረት ለጦርነቱ በላማናውያን ላይ ተዘ
ጋጅተው ነበር።
፱ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን፣ ወይ
ንም አማሊቅያውያን በአንደዚህ ዓይነቱ
የጦርነት ዝግጅት እጅግ ተገርመው ነበር።
፲ እንግዲህ ንጉስ አማሊቅያ ሀከኔፊ ምድር
ከሠራዊቱ ፊት የሚመጣ ቢሆን ኖሮ፣ ምና
ልባት ላማናውያን የኔፋውያንን አሞኒሀ
ከተማ እንዲያጠቁ ያደርግ ነበር፣ እነሆ
እርሱ ለህዝቡ ደም ምንም ደንታ የለው
ምና።
፲፩ ነገር ግን እነሆ፣ አማሊቅያ እራሱ ወደ
ጦርነቱ አልመጣም። እናም እነሆ፣ ዋናው
ሻምበሉ በአሞኒሀ ከተማ ኔፋውያንን ለማጥ
ቃት አልደፈረም፤ ሞሮኒ በኔፋውያን የሚ
ደረጉትን ጉዳዮች በመቀየሩ፣ ላማናውያን
በአፈገፈጉበት ስፍራ ተቆጥተውና በእነርሱ
ላይ ለመምጣት አልቻሉም ነበር።
፲፪ ስለዚህ ላማናውያን ወደ ምድረበዳው
አፈገፈጉ፣ እናም የጦር ስፍራቸውን ወሰ
ዱና፣ በሁለተኛ ደረጃ ኔፋውያንን ለማጥ
ቃት የሚመች ጥሩ ስፍራ ብለው ወደ ገመ
ቱት የኖህ ምድር ቀጠሉ።
፲፫ ላማናውያን ሞሮኒ ም ሆነ፣ የደህንነት
ምሽግ በምድሪቱ ሁሉ ባሉት እያንዳንዱ
ከተማ ዙሪያ ሀመመሸጉን አላወቁም ነበር፤
ስለዚህ፣ በቆራጥ ውሳኔ ወደ ኖህ ምድር
ዘመቱ፤ አዎን፣ የላማናውያን ዋና ሻምበል

፵፱ ፫ሀ አልማ ፲፮፥ ፪–፫፣ ፱፣ ፲፩።
፰ሀ አልማ ፵፰፥ ፯–፲።
፲ሀ ፪ ኔፊ ፭፥ ፰፤
ኦምኒ ፩፥ ፲፪፤
አልማ ፵፯፥ ፩።
፲፫ሀ አልማ ፵፰፥ ፰።

መጣ፣ እናም የከተማዋን ህዝብ ለማጥፋት መሃላ አደረገ።

፲፩ ነገር ግን እነሆ፣ በሚገርማቸው ሁኔታ፣ የኖህ ከተማ፣ ደካማ ስፍራ የነበረ ችው፣ አሁን፣ በሞሮኒ አማካኝነት፣ ጠን ካራ ሆነች፣ አዎን፣ ከአሞኒሀም ከተማ እን ኳን በመብለጥ ጠንካራ ሆነች።

፲፪ እናም እንግዲህ፣ እነሆ፣ ይህ በሞ ሮኒ የነበረ ብልህ ሁኔታ ነበር፤ ምክንያቱም እነርሱ በአሞኒህ ከተማ ይፈራሉ፤ እናም እስከአሁን የኖህ ከተማ የምድሪቱ ደካማው ክፍል በመሆኑ፣ ስለዚህ በዚያ ስፍራ ለመ ዋጋት ይሄዳሉ ብሎ ገምቶ ነበር፣ ይህም ነገር የሆነው ሞሮኒ እንደተመኘው ነበር።

፲፫ እናም እነሆ፣ ሞሮኒ ሌሂን በከተ ማዋ ላይ ዋና ሻምበል በማድረግ ሾሞት ነበር፤ እናም በሲዶም ወንዝ በስተምስራቅ ባለው ሸለቆም ከላማናውያን ጋር የተዋጋው ᴴይኸው ሌሂ ነበር።

፲፬ እናም እንግዲህ እነሆ እንዲህ ሆነ፣ ሌሂ ከተማዋን ማስተዳደሩን ላማናውያን ባወቁ ጊዜ በድጋሚ ተቆጡ፣ ምክንያቱም ሌሂን እጅግ ይፈሩት ነበር፤ ይሁን እንጂ ዋናው ሻምበላቸው ከተማዋን ለማጥቃት መሃላ ምሎ ነበር፤ ስለዚህ፣ እነርሱም ሠራ ዊታቸውን አምጥተው ነበር።

፲፭ እንግዲህ እነሆ፣ ላማናውያን የተገነ ባው ግንብ ረጅም በመሆኑ፣ እናም በዙሪ ያው የተቆፈረው ኩሬ ጥልቅ በመሆኑ በመ ግቢያው በኩል ካልሆነ በቀር ወደ ደህንነ ታቸው ምሽግ በሌላ መንገድ መግባት አል ቻሉም።

፲፮ እናም ኔፋውያን ወደ ምሽጉ ላይ ድን ጋይና ቀስቶቻቸውን በመጣል በማንኛውም መንገድ ለመውጣት የሚሞክሩ ሰዎችን ሁሉ ለማጥፋት ተዘጋጅተው ነበር።

፲፯ ስለዚህም፣ አዎን፣ ጠንካራ ሰዎቻቸ ውም፣ በጎራዴዎቻቸው እናም በወንጭፎ ቻቸው፣ በመግቢያው በኩል ወደ ደህንነት ቦታቸው ለመምጣት የሚሞክሩትን ሁሉ ለመምታት ተዘጋጅተው ነበር፤ እናም ከላ ማናውያን እራሳቸውን ለመከላከል እንደ ዚህ ተዘጋጅተው ነበር።

፲፰ እናም እንዲህ ሆነ የላማናውያን ሻምበሎች ወታደሮቻቸውን መግቢያው በር ድረስ አምጥተዋቸው ነበር፣ እናም ወደ ደህንነት ስፍራቸውን ለመግባት ከኔ ፋውያን ጋር መጣላት ጀመሩ፤ ነገር ግን እነሆ፣ በኃይል እስከሚገደሉም ድረስ በተደጋገመ ጊዜ ወደኋላ እንዲሸሹ ተደ ርገዋል።

፲፱ እንግዲህ በመግቢያው በኩል በኔ ፋውያን ላይ ድል መቀዳጀት አለመቻ ላቸውን ባወቁ ጊዜ፣ ወደሰራዊታቸው መድረስ ይችሉ ዘንድ ለመዋጋትም እኩል እድል እንዲያገኙ ምሽጎቻቸውን ቆፈሩት፤ ነገር ግን እነሆ፣ በዚህ ሙከራቸው በላያ ቸው ላይ በተወረወረባቸው ድንጋይና የጦር ቀስት ተደመሰሱ፤ እናም አፈሩን በመግ ፋት ጉድጓዱን ከመሙላት ይልቅ በተወ ሰነ ደረጃ በቆሰሉና በሞቱ ሰዎች ጉድጓ ዱን ሞሉት።

፲፲ ኔፋውያን በጠላቶቻቸው ላይ ሁሉ እንዲህ ሀይል ነበራቸው፤ እናም ላማና ውያን ዋና ሻምበሎቻቸው በሙሉ እስ ከሚገደሉ ድረስ ኔፋውያንን ለማጥፋት ሞከሩ፤ አዎን፣ እናም ከአንድ ሺህ የሚበ ልጡ ላማናውያን ተገደሉ፤ በሌላ መልኩ፣ ከኔፋውያን አንድም ነፍስ እንኳን አልጠ ፋም ነበር።

፲፳ በመግቢያው በኩል ለላማናውያን ቀስ ቶች የተጋለጡ ሀምሳ የሚጠጉ ሰዎች ቆስ ለው ነበር፤ ነገር ግን በጋሻዎቻቸው፣ እናም በደረት ኪሶቻቸውና፣ በቆቦቻቸው ተከል ለው ስለነበር፣ ቁስሎቻቸው ሁሉ በእግሮ ቻቸው ላይ ነበር፣ ብዙዎቹም በጣም ቆስ ለው ነበር።

፲፳፩ እናም እንዲህ ሆነ፣ ዋና ሻምበሎ ቻቸው በሙሉ መገደላቸውን ላማናውያን በተመለከቱ ጊዜ ሁሉም ወደ ምድረበዳው ሸሹ። እናም እንዲህ ሆነ፣ በትውልዱ ኔፋ ውያን ለሆነው አማሊቅያ ንጉሳቸው ስለታ

ላቁ ሽንፈታቸው ለመናገር ወደ ኔፊ ምድር ተመለሱ።

፳፯ እናም እንዲህ ሆነ እርሱም በኔፋውያን ላይ ፍላጎቱን ባለማግኘቱ በህዝቡ እጅግ ተቆጥቶ ነበር፤ እርሱም በባርነት ቀንበር ስር እንዲሆኑ አላደረጋቸውም ነበር።

፳፰ አዎን፣ እጅግ ተቆጥቶ ነበር፣ እናም እግዚአብሔርንና፣ ደግሞ ሞሮኒን [ሀ]ረገመ፣ ደሙንም እጠጣለሁ ብሎ [ለ]መሃላ ፈፅሞ ነበር፤ እናም ይህም የሆነው ለህዝቡ ደህንነት ሲል ሞሮኒ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት በመጠበቁ ነበር።

፳፱ እናም እንዲህ ሆነ በሌላ መልኩ የኔፊ ህዝብ ወደር በሌለው ኃይሉ ከጠላቶቻቸው እጅ ስላስለቀቃቸው ጌታ አምላካቸውን [ሐ]አመሰገኑ።

፳፱ እናም በኔፊ ህዝብ ላይ የመሣፍንቱ የአስራ ዘጠነኛው የንግስ ዘመን ተፈፀመ።

፴ አዎን፣ እናም በሔለማንና፣ በሺብሎን፣ እናም በቆሪያንቶንና፣ በአሞን እንዲሁም በወንድሞቹ፣ አዎን፣ እናም በንስሀ በመጠመቅና ከህዝቡ መካከል እንዲሰብኩ በተላኩት [ሀ]በቅዱሱ የእግዚአብሔር ስርዓት በተሾሙት ሁሉ የታወጁትን የእግዚአብሔር ቃላት በትህትና ስላዳመጡ በህዝብ መካከል የማያቋርጥ ሰላም፣ እናም በቤተክርስቲያኗ እጅግ ታላቅ ብልፅግና ነበር።

ምዕራፍ ፴

ሞሮኒ ለኔፋውያን ምድር ምሽግ አደረገ—ኔፋውያን ብዙ አዳዲስ ከተሞችን ሰሩ—በኔፋውያን ላይ በክፋታቸውና በእርኩሰታቸው ዘመን ጦርነትና ጥፋት አረፈባቸው—ሞሪያንተንና ተቃዋሚዎቹ በቴአንኩም ተሸነፉ—ኔፋኢያህ ሞተ፣ እናም ልጁ ፓሆራን የፍርድ ወንበሩን ያዘ። ከ፳፫–፳፯ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም አሁን እንዲህ ሆነ ሞሮኒ ለጦርነት መዘጋጀቱንም ሆነ ህዝቡን ከላማናውያን መከላከሉን አላቆመም፤ በመሣፍንቱ ሀያኛ ዓመት የንግስና ዘመን መጀመሪያ ወታደሮቹ እንዲጀምሩ በማድረጉ፣ በኔፋውያን የተያዙትን ምድር ሁሉ የተቆለለውን አፈር በከተማው ዙሪያ መቆፈር እንዲጀምሩ አደረገ።

፪ እናም በተቆለለው አፈር በጫፉ ላይ ግንድ እንዲሆን አደረገ፤ አዎን፣ በከተማው ዙሪያ በሰው ቁመት የተሰራ የእንጨት አጥር እንዲሆን አደረገ።

፫ ከእንጨት በተሰራው ላይ በግንዱ ዙሪያ ሹል እንጨት እንዲሰራ አደረገ፤ እናም የሾለው እንጨት ጠንካራና ከፍ ያለ ነበር።

፬ እናም በሹል እንጨት የተሰሩትን እንዲከልሉ ምሶሶ እንዲቆም አደረገ፤ እናም የላማናውያን ድንጋይና ቀስቶች የሞሮኒን ወታደሮች መምታት እንዳይችሉ በማማዎቹ ላይ የጥበቃ ስፍራ እንዲሆን አደረገ።

፭ እናም ማማው እንደ ፍላጎታቸውና ብርታታቸው፣ በከተማዋ ግንብ ለመጠጋት የሞከሩትን ለመግደል ከላይ ሆነው ድንጋይ ለመወርወር እንዲችሉ ሆኖ ነበር የተዘጋጀው።

፮ በምድሪቱ ሁሉ ባሉት ከተሞች ዙሪያ ሞሮኒ ጠላቶችን ለመከላከል ጠንካራ ምሽግ እንደዚህ አዘጋጅቶ ነበር።

፯ እናም እንዲህ ሆነ ሞሮኒ ወታደሮቹ በምድረበዳው ወደ ምስራቅ እንዲሄዱ አደረገ፤ አዎን፣ እናም በራሳቸው ምድር በስተምስራቅ በምድረበዳው የነበሩትን ላማናውያን ሁሉ በዛራሔምላ ምድር በስተደቡብ ወደነበረው ወደራሳቸው ምድር አስወጡአቸው።

፰ እናም የኔፊ ምድር ከምስራቅ ባህር እስከ ምዕራብ ባህር ድረስ በቀጥተኛ መንገድ የተቋቋመ ነበር።

፱ እናም እንዲህ ሆነ ሞሮኒ ላማናውያንን በስተሰሜን ከነበረው ርስታቸው ሁሉ በምስራቅ በኩል ከምድረበዳው ባስወጣቸው ጊዜ፣ በዛራሔምላ ምድር የሚኖሩ ነዋሪ

፳፯ ሀ ቅ.መ.መ. መስደብ። ለ የሐዋ. ፳፫፡ ፲፪።

፳፰ ሀ ቅ.መ.መ. አመስጋኝ፣ ምስጋናን፣ ምስጋና

መስጠት። ፴ ሀ አልማ ፵፫፡ ፪።

ዎችንና በምድሪቱ ዙሪያ ያሉትን በስተ ምስራቅ በምድረበዳው እስከ ባህሩ ዳርቻ ድረስም እንኳን እንዲጓዙ እናም ምድሪ ቱን እንዲወርሱ አደረገ።

፲ እናም ደግሞ በስተደቡብ በራሳቸው ምድር ዳርቻ ሠራዊቱን አስቀመጠና፣ ከጠ ላቶቻቸው እጅ ወታደሮቹንና ህዝቡን ይጠ ብቅ ዘንድ ᵐምሽግ እንዲሰሩ አደረገ።

፲፩ እናም በምድረበዳው በምስራቅ እናም ደግሞ በስተምዕራብ በኩል የላማናውያን ጠንካራ ምሽጎችን አጠፋ፣ አዎን፣ በኔፋው ያንና በላማናውያን መካከል፣ በዛራሔምላ ምድርና በኔፊ ምድር መካከል፣ ከባህሩ ከምዕራብ ጀምሮ እስከሲዶም ወንዝ ጫፍ መሸገ—ኔፋውያን በሰሜን በኩል ያለውን መሬት በሙሉ፣ አዎን፣ እንደፍላጎታቸ ውም ከለጋስ ምድር በስተሰሜን በኩል ያለ ውን ምድር በሙሉ ያዙ።

፲፪ ሞሮኒ በየቀኑ በቁጥር ከሚጨምሩት ሠራዊቶቹ ጋር፣ ስራው ለእነርሱ የጥበቃ ማረጋገጫ በመሆኑ፣ ላማናውያንን ከራሳ ቸው ምድር በምድራቸውም ባሉት ሀብቶ ቻቸው ላይ ስልጣን እንዳይኖራቸው ጉል በታቸውን፣ እናም ስልጣናቸውን ለማጥ ፋት ፈለገ።

፲፫ እናም እንዲህ ሆነ ኔፋውያን የከተማ ዋን መሰረት ጀመሩና፣ የከተማዋንም ስም ሞሮኒ ብለው ጠሯት፤ እናም ይህ በባህሩ በስተምስራቅ በኩል ነበር፤ እናም በላማና ውያን ይዞታ ሥር በሆነው በደቡብ ዳርቻ ነበር።

፲፬ እናም ደግሞ የአሮንንና የሞሮኒን ወሰን የሚያገናኘውን በሞሮኒና በአሮን ከተማ መካከል የከተማ መሰረትን ጀመሩ፤ እናም የከተማዋን ወይም የምድሪቱን ስም ኒፋአ ያህ ብለው ጠሯት።

፲፭ እናም ደግሞ በዚያው ዓመት በስ ተሰሜን በኩል ብዙ ከተሞችን መስራት ጀመሩ፣ አንድ በተለየ ሁኔታ የሰሩትን ሌሂ ብለው ጠሩት፣ ይህም በባህሩ ሰርጥ ዳርቻ በስተሰሜን በኩል ነበር።

፲፮ እናም ሀያኛው ዓመት እንደዚህ ተፈ ፀመ።

፲፯ እናም በመሣፍንቱ ሀያ አንደኛ ዓመት መጀመሪያ የንግስና ዘመን ላይ የኔፊ ህዝብ በእንደዚህ ዓይነት ብልጽግና ላይ ነበር።

፲፰ እናም እጅግ በለፀጉ፣ እናም እጅግም ሀብታም ሆኑ፣ አዎን፣ እናም በምድሪቱ ላይ ተባዙና በረቱ።

፲፱ እናም ጌታ ለሰው ልጆች ያደረገውን ቃል በሙሉ ለመፈፀም እንዴት መሀሪና ፍትሀዊ እንደሆነ እንመለከታለን፤ አዎን፣ ለሌሂ በዚህ ጊዜም እንኳን ቢሆን፣ እንዲህ ብሎ የተናገራቸው ቃላት የተረጋገጡ መሆ ናቸውን ለመመልከት እንችላለን፥

፳ አንተ እና ልጆችህ የተባረካችሁ ናችሁ፤ እናም እነርሱ የተባረኩ ይሆናሉ፣ ትዕዛዛቴንም እስከጠበቁ ድረስ በምድሪቱ ላይ ይበለፅጋሉ። ነገር ግን ትዕዛዛቴን እስ ካልጠበቁ ድረስ ከጌታ ፊት ᵐእንደሚለዩ አስታውሱ።

፳፩ እናም እነዚህ ቃል ኪዳኖች ለኔፊ ህዝብ እውነትነታቸው እንደሚረጋገጥ እና ያለን፤ ይህ በመካከላቸው የነበረው ፀብና ጥል፤ አዎን፣ ግድያቸውና፣ ዝርፊያቸው፣ ጣኦት አምላኪነታቸውና፣ እርኩሰታቸው በእነርሱም ላይ ጦርነትና ጥፋትን አምጥ ቶባቸው ነበርና።

፳፪ እናም በሺህ የሚቆጠሩ ኃጢአተ ኞች ወንድሞቻቸው በባርነት በተመደቡ፣ ወይም በጎራዴ በጠፉ፣ ወይም እምነት አጥ ተው በመነመኑ፣ እናም ከላማናውያን ጋር በተቀላቀሉ ጊዜ የጌታን ትዕዛዛት በመጠ በቅ ታማኝ የነበሩት እነዚያ በሁሉም ጊዜ ድነዋል።

፳፫ ነገር ግን እነሆ እንደሞሮኒ ጊዜ አዎን፣ በመሣፍንቱ በሀያ አንደኛ የንግስና ዘመን በዚህ ጊዜም እንኳን፣ ከኔፊ ጊዜ ጀምሮ በኔፊ ሰዎች መካከል በጭራሽ እንዲህ ያለ ᵐደስታ አልነበረም።

፳፬ እናም እንዲህ ሆነ የመሣፍንቱ ሀያ ሁለተኛ የንግስና ዘመንም እንዲህ በሰላም

ᵐ ፲ ሀ አልማ ፵፱፣ ፲፰–፳፪። ᵐ ሀ ት. እና ቃ. ፩፣ ፲፩። ᵐ ሀ ሞዛያ ፪፣ ፵፩።

ተፈፀመ፤ አዎን፣ እናም ደግሞ ሀያ ሶስተኛው ዓመት።

፳፭ እናም እንዲህ ሆነ በመሣፍንቱ ሀያ አራተኛ የንግስና ዘመን መጀመሪያ ላይ፣ በሌሂ ምድር ዳርቻ ላይ ተገጣጥመው በነበሩት የሌሂን ምድር እና የሞሪያንተንን ምድር በተመለከተ በኔፊ ህዝብ መካከል በተፈጠረው ᐟᐟፀብ ባይሆን ኖሮ በኔፊ ህዝብ መካከል ሰላም በሆነ ነበር፤ ሁለቱም በባህሩ ሰርጥ ዳርቻ ነበሩ።

፳፮ እነሆም፣ የሞሪያንተንን ምድር የራሳቸው ያደረጉት ሰዎች ከሌሂ ምድር ትንሹን ክፍል ይገባናል ብለው ነበር፤ ስለዚህ የሞሪያንተን ህዝብ በወንድሞቻቸው ላይ ጦር እስኪያነሱ ድረስ በመካከላቸው የጋለ መጣላት ተጀምሮ ነበር፣ እናም በጎራዴዎቻቸው እነርሱን ለመግደል ቆርጠው ነበር።

፳፯ ነገር ግን እነሆ፣ የሌሂን ምድር የያዙት ሰዎች ወደ ሞሮኒ የጦር ሰፈር ሸሹ፣ እናም እርዳታን ለማግኘት ለእርሱ አቤት አሉ፤ እነሆ አልተሳሳቱም ነበርና።

፳፰ እናም እንዲህ ሆነ፣ ሞሪያንተን ተብሎ በሚጠራው ሰው የተመሩት የሞሪያንተን ህዝብ፣ የሌሂ ህዝብ ወደ ሞሮኒ የጦር ሰፈር መሸሻቸውን ባወቁ ጊዜ፣ የሞሮኒ ወታደሮች በእነርሱ ላይ እንደሚመጡ እናም እንዳያጠፉአቸው እጅግ ፈርተው ነበር።

፳፱ ስለዚህ፣ ሞሪያንተን ወደሰሜን በትልቅ ውኃ ወደተሸፈነው ስፍራ እንዲሸሹ እናም በስተሰሜን በኩል ያለውን መሬት እንዲይዙ ልባቸውን አነሳሳ።

፴ እናም እነሆ፣ ይህንን ዕቅድ (ለሃዘን ምክንያት ይሆን የነበረውን) እንዲፈፀም ማድረግ ይችሉ ነበር፣ ነገር ግን እነሆ፣ ሞሪያንተን ስሜታዊ ስለነበር፣ እነሆም በአንዲት ገረዱ ተቆጣ፣ እናም ክፉኛ መታት።

፴፩ እናም እንዲህ ሆነ እርሷ ሸሸችና፣ ወደ ሞሮኒ የጦር ሰፈር መጣች፣ እናም የሆነውን ሁሉ በተመለከተና፣ ደግሞ ወደ ሰሜን ለመሸሽ ያላቸውን ሙከራ ለሞሮኒ ነገረችው።

፴፪ እንግዲህ በለጋስ ወይም በሞሮኒ የነበሩ ሠዎች የሞሪያንተንን ቃል በመስማት እናም ከህዝቡም ጋር ይቀላቀላሉ፣ እናም ከኔፋውያን ጋር የከፋ ሁኔታን ሊያስከትል የሚችል የምድር ክፍሎችን ያገኛሉ፣ አዎን፣ ውጤቱም ᐟᐟለነፃነታቸው ውድቀት መንስኤ ሊሆን የሚችል ነው ብለው ፈርተው ነበር።

፴፫ ስለዚህ ሞሮኒ፣ ከጦር ሰፈራቸው፣ የሞሪያንተንን ሰዎች እርምጃ ለማቋረጥ፣ ወደ ሰሜን ክፍል እንዳይሸሹም ለማቆም ወታደር ላከ።

፴፬ እናም እንዲህ ሆነ ወደ ᐟᐟወደመው ምድር ወሰን እስከሚመጡ ድረስ አላቋረጧቸውም ነበር፤ እናም በምድሪቱ ሰሜን በኩል በቀጭኑ የባህሩ ማለፊያ በኩል አዎን፣ በባህሩ በኩል በስተምዕራብና በስተምስራቅ በኩል እርምጃቸውን አቋረጡ።

፴፭ እናም እንዲህ ሆነ በሞሮኒ የተላኩት ሠራዊቶች፣ ቴአንኩም ተብሎ በሚጠራ ሰው የተመሩት፣ የሞሪያንተንን ህዝብ አገኙ፤ እናም የሞሪያንተንም ህዝብ ግትር ነበር፣ በእርሱ (በኃጢአተኛና በሸንጋይ ቃላቱ በመቀስቀሳቸው የተነሳ) ጦርነቱም በመካከላቸው ሆነ፣ በዚያም ቴአንኩም ሞሪያንተንን ገደለውና፣ ወታደሮቹን አሸነፈ፣ እናም በምርኮም ወሰዱአቸውና፣ ወደ ሞሮኒ የጦር ሰፈር ተመለሱ። እናም በዚሁ የመሣፍንቱ ሀያ አራተኛው የንግስና ዘመን በኔፊ ህዝብ ላይ ተፈፀመ።

፴፮ እናም የሞሪያንተንን ህዝብ እንደዚህ ነበር የተመለሱት። እናም ሰላሙን ለመጠበቅ ቃል ኪዳን ከገቡ በኋላ ወደ ሞሪያንተን ምድር ተመለሱና፣ በእነርሱና በሌሂ ህዝብ መካከል አንድነት ሆነ፤ እናም ደግሞ የሌሂ ህዝብ ወደራሳቸው ምድር ተመለሱ።

፴፯ እናም እንዲህ ሆነ የኔፊ ህዝብ ሰላምን መልሰው በመሰረቱበት በዚሁ ዓመት፣ በእግዚአብሔር ፊት ፍፁም ትክክል በሆነ ሁኔታ የፍርድ ወንበሩን ቦታ ይዞ የነበረው ሁለተኛው ዋና ዳኛም ኒፋአያህ ሞተ።

፳፭ ᐟᐟ ቅ.መ.መ. ጸብ። ፴፪ ᐟᐟ ቅ.መ.መ. መብት። ፴፩ ᐟᐟ አልማ ፶፯፣ ፲፯።

፴፰ ይሁን እንጂ፣ እናም በአልማና በአ
ባቱ ከሁሉም ነገር በላይ ቅዱስ ተደርገው
የተገመቱትን መዝገቦች ከአልማ አልቀበ
ልም ብሎ ነበር፤ ስለዚህ አልማ እነዚህን
ነገሮች ለልጁ ሔለማን ሰጠው።

፴፱ እነሆ፣ እንዲህ ሆነ የኒፋአያህ ልጅ
በአባቱ ቦታ የፍርድ ወንበሩን እንዲይዝ
ተመደበ፤ አዎን በትክክል እንዲፈርድና፣
ሰላምንና፣ የህዝቡን ነፃነት እንዲጠብቅ፣
እናም ጌታ አምላካቸውን ለማምለክ ቅዱስ
የሆነውን ልዩ መብታቸውን እንዲፈቅድላ
ቸው፣ አዎን፣ በጊዜው ሁሉ እግዚአብሔ
ርን ምክንያት እንዲደግፍና እንዲከላከል፣
እናም ኃጢአተኞችን እንደወንጀላቸው ወደ
ፍርድ ለማምጣት፣ በመሀላና፣ በቅዱስ ስር
ዓት ዋና ዳኛ በመሆንና፣ በህዝቡ ላይ ገዢ
ሆኖ ተሹሞ ነበር።

፴ እንግዲህ እነሆ፣ ስሙም ፓሆራን
ተብሎ ይጠራ ነበር። እናም ፓሆራን የአ
ባቱን ወንበር ያዘና፣ በሀያ አራተኛ ዓመት
መጨረሻም በኔፊ ህዝብ ላይ የንግስናውን
ዘመን ጀመረ።

ምዕራፍ ፶፩

*የንጉሱ የሆኑትን ሰዎች ህጉን ለመለወጥ
እናም ንጉሥን ለመምረጥ ፈለጉ—ፓሆ
ራን እናም የነበረውን መንግስት የሚ
ደግፉት በህዝቡ ድምፅ ተደግፈው
ነበር—ሞሮኒ የንጉሱ የሆኑትን ሰዎች
ሀገራቸውን እንዲከላከሉ አለበለዚያም
እንዲገደሉ አስገደዳቸው—አማሊቅያ
እናም ላማናውያን ብዙ የተመሸጉ ከተ
ማዎችን ያዙ—ቴአንኩም የላማናውያንን
ወረራ መለሰ እናም አማሊቅያን በድንኳኑ
ውስጥ ገደለው። ከ፳፯–፳፯ ም.ዓ. ገደማ።**

፩ እናም እንግዲህ እንዲህ ሆነ በኔፊ ህዝብ
ላይ በመሣፍንቱ ሀያ አምስተኛ ዓመት የን
ግስና ዘመን መሬታቸውን በተመለከተ
በሌሂና በሞሪያንተን ህዝብ መካከል ሰላ
ምን መሰረቱ፣ እናም ሀያ አምስተኛውን
ዓመት በሰላም ጀመሩ፤

፪ ይሁን እንጂ፣ የኔፊ ህዝብ በምድሪቱ
በሙሉ ለረጅም ጊዜ ሰላምን ማቆየት አል
ቻሉም፣ ምክንያቱም ዋናውን ዳኛ ፓሆራ
ንን በተመለከተ በህዝቡ መካከል ፀብ ተጀ
መረ፤ እነሆ፣ ከህዝቡ የተወሰነው ክፍል
በህጉ ጥቂት ነጥቦች እንዲለወጡ ፈልገው
ነበርና።

፫ ነገር ግን እነሆ፣ ፓሆራን ህጉን አልለ
ወጠም፣ እንዲለወጥም አልፈቀደም ነበር፤
ስለዚህ፣ የህጉን መለወጥ በተመለከተ ከአ
ቤቱታቸው ጋር ድምፃቸውን የላኩትንም
አላዳመጣቸውም ነበር።

፬ ስለዚህ፣ ህጉ እንዲለወጥ የፈለጉት በእ
ርሱ ተቆጥተው ነበር፤ እናም በምድሪቱ ላይ
ከእንግዲህ ዋና ዳኛ እንዲሆን አልፈለጉም፤
ስለዚህ ይህንን በተመለከተ የጋለ ፀብ ተነሳ፣
ነገር ግን እስከ ደም መፋሰስ አልነበረም።

፭ እናም እንዲህ ሆነ ፓሆራን ከፍርድ
ወንበር ዙፋን እንዲወርድ ፈልገው የነበ
ሩት የንጉሱ ሰዎች ተብለው ይጠሩ ነበር፤
ምክንያቱም ህጉ ነፃ መንግስቱን በመጣል
እናም ምድሪቱም በንጉስ እንዲገዛ ፈል
ገው ነበር።

፮ እናም ፓሆራን በምድሪቱ ላይ ዋና
ዳኛ ሆኖ እንዲቀር የሚፈልጉ ለራሳቸው
ነፃ ሰዎች የሚለውን ስም ወስደው ነበር፤
እናም እንደዚህ በመካከላቸው ክፍፍል
ነበር፣ ምክንያቱም ነፃ ሰዎቹ መብታቸ
ውንና፣ በነፃው መንግስት የኃይማኖታቸ
ውን ነፃነት ለመጠበቅ መሀላ እንዲሁም ቃል
ኪዳን ገብተው ነበርና።

፯ እናም እንዲህ ሆነ እንዲህ ዓይነቱ
ፀብ በህዝቡ ድጋፍ መልስ አግኝቶ ነበር።
እናም እንዲህ ሆነ የህዝቡ ድምፅ የነፃ ሰዎ
ችን ደገፈና፣ ፓሆራን የፍርድ ወንበር ያዘ፣
ይህም በፓሆራን ወንድሞች እናም በነፃ
ነት ሰዎች መካከል ታላቅ ደስታን ፈጠረ፤
ደግሞም ብዙዎቹ የነፃነት ሰዎች ንጉሳዊ
የሆነውን ስርዓት እንዳይቃወሙ፣ ነገር
ግን የነፃነቱን መንስኤ እንዲከላከሉ ተገ
ደው ነበር።

፰ እንግዲህ ንጉሶቹን ይደግፉ የነበሩት፣

[ሀ]በትውልድ ታላቅ ስፍራ የነበራቸው፤ እናም ንጉስ ለመሆንም የፈለጉ ነበሩ፤ እናም ኃይልንና ስልጣንን በህዝቡ ላይ በሚፈልጉትም ይደገፉ ነበር።

፱ ነገር ግን እነሆ፣ ይህ በኔፊ ህዝብ መካከል እንደዚህ ዓይነቱ ፀብ ወሳኝ የሆነበት ጊዜ ነበር፤ ምክንያቱም እነሆ፣ አማሊቅያ የላማናውያን ሰዎችን ልብ በኔፊ ህዝብ ላይ በድጋሚ አነሳስቶ ነበር፤ እናም ከምድሪቱ ከሁሉም ክፍል ወታደሮችን በአንድ ላይ ሰበሰበና፣ አስታጠቃቸው፣ እናም በሙሉ ትጋቱ ለጦርነት አዘጋጃቸው፤ ምክንያቱም የሞሮኒን ደም ለመጠጣት [ሀ]ምሎ ነበርና።

፲ ነገር ግን እነሆ፣ እርሱ የገባው ቃል ኪዳን የተጣደፈ መሆኑን እንመለከታለን፤ ይሁን እንጂ እራሱን እና ወታደሮቹን ከኔፋውያን ጋር ለመዋጋት አዘጋጀ።

፲፩ አሁን የእርሱ ወታደሮች ከዚህ ቀደም እንደነበሩት ታላቅ አልነበሩም፣ ምክንያቱም ብዙ ሺዎች በኔፋውያን ተገድለው ነበርና፤ ነገር ግን ታላቅ ውድቀት ቢደርስባቸውም፣ አማሊቅያ ወደ ዛራሔምላ ምድር ለመምጣት የማይፈራ እስከሚሆን ድረስ፣ በሚያስገርም ሁኔታ ብዙ ወታደሮችን በአንድነት ሰብስቦ ነበር።

፲፪ አዎን፣ አማሊቅያም ቢሆን ራሱ ላማናውያንን በመምራት መጥቶ ነበር። እናም ይህም የነበረው በመሣፍንቱ የሀያ አምስተኛ ዓመት የንግስና ዘመን ነበር፤ እናም በዚሁ ጊዜ ነበር ኔፋውያን ዋና ዳኛ የነበረውን ፓሆራንን በተመለከተ ለፀባቸው መፍትሔ መፈለግ የጀመሩት።

፲፫ እናም እንዲህ ሆነ የንጉሱ ሰዎች ተብለው የሚጠሩት ሰዎች ላማናውያን ከእነርሱ ጋር ለመዋጋት መምጣታቸውን በሰሙ ጊዜ በልባቸው ተደስተው ነበር፤ እናም በዋናው ዳኛና፣ ደግሞ [ሀ]በነፃነቱ ሰዎች፣ እጅግ በመቆጣታቸው የጦር መሳሪያቸውን ለማንሳት አልፈቀዱም፣ ሀገራቸውንም ለመከላከል የጦር መሳሪያዎችን አላነሱም ነበር።

፲፬ እናም እንዲህ ሆነ ሞሮኒ ይህንን፣ እናም ደግሞ በምድሪቱ ዳርቻ ላማናውያን መምጣታቸውን በተመለከተ ጊዜ፣ እነርሱን ለመጠበቅ በታላቅ ትጋት ከእርሱ ጋር አብረው የሰሩት ሰዎች ግትር በመሆናቸው እጅግ ተቆጥቶ ነበር፤ አዎን፣ በእጅግ ተቆጥቶ ነበር፤ ነፍሱም በእነርሱ ላይ በቁጣ ተሞልታ ነበር።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ ሞሮኒ ወደ ምድሪቱ ገዢ እንዲያነበው የፈለገውን፣ እናም ሀገራቸውን ለመከላከል የሚቃወሙትን እንዲያስገድድ፣ አለበለዚያም እንዲገድላቸው ለእርሱ (ለሞሮኒ) ስልጣንን እንዲሰጠው ከህዝቡ ድጋፍ ጋር አቤቱታውን ላከ።

፲፮ በህዝቡ መካከል እንደዚህ ዓይነቱን ፀብና ተቃውሞ ማቆም የእርሱ የመጀመሪያው ጥንቃቄ ነበር፤ እነሆ ይህ ከዚህ ቀደም የጥፋታቸው ሁሉ መንስኤ ስለነበር ነው። እናም እንዲህ ሆነ በህዝቡም ድምፅ የተነሳ ይህ ተፈቅዶ ነበር።

፲፯ እናም እንዲህ ሆነ ሞሮኒ የንጉሱን ሰዎች፣ ትምክህታቸውንና፣ ክብራቸውን እንዲያጠፉ፣ እናም እንዲገድሉአቸው፣ አለበለዚያም የጦር መሳሪያዎቻቸውን እንዲወስዱና፣ ነፃነታቸውን እንዲደግፉ እንዲያደርጉ ወታደሮቹን አዘዛቸው።

፲፰ እናም እንዲህ ሆነ ሠራዊቱ በሰዎቹ ላይ ዘመቱ፤ እናም እነርሱ ትምክህታቸውንና ክብራቸውን እንደዚህ ያህል ገፈፉባቸው፣ ከሞሮኒ ሰዎች ጋር ለመዋጋት የጦር መሳሪያዎቻቸውን ሲያነሱ በጎራዴዎቻቸው ድባቅ ተመቱና ተገደሉ።

፲፱ እናም እንዲህ ሆነ [ሀ]ከተቃዋሚዎቹ አራት ሺህ የሚሆኑት በጎራዴው ተመትተው ነበር፤ እናም በጦርነቱ ያልተገደሉት መሪዎቻቸውን በዚህን ጊዜ እነርሱን ለፍርድ ለማቅረብ ጊዜ ባለመኖሩ ተወስደውና ወደ ወህኒ ቤቱ ተጣሉ።

፳ እናም ከተቃዋሚዎቹ የተቀሩት፣ በጎራዴ ተመትተው ከተገደሉት ይልቅ፣

፶፩ ፰ሀ ቅ.መ.መ. ኩራት።
፱ሀ አልማ ፵፱፥ ፳፮–፳፯።
፲፫ሀ አልማ ፵፮፥ ፲–፲፮።
፲፱ሀ አልማ ፰፥ ፲፮።

[ሀ]የነፃነት አርማን ደገፉ፣ እናም በምሶሶዎ ቻቸው ላይና፣ በከተሞቻቸው ላይ የነፃነት አርማቸውን እንዲሰቅሉና፣ ሀገራቸውን ለመከላከል የጦር መሳሪያዎቻቸውን እን ዲያነሱ ተገደዱ።

፳፩ እናም የንጉሱ ሰዎች ተብለው በመ ጠራት ዳግም እንዳይታወቁ ሞሮኒ የን ጉሱ ሰዎች የሆኑትን ፍፃሜ አደረገ፤ እናም የልዕልነት ደም አለን በሚሉት ትምክህተ ኛና ግትር ሰዎች ላይ እንደዚህ መጨረሻ ቸውን አደረገ፤ ነገር ግን እንደ ወንድሞቻ ቸው እራሳቸውን ትሁት ማድረግና፣ ከባ ርነት ለመላቀቅ በጀግንነት እንዲዋጉ አደ ረጋቸው።

፳፪ እነሆ፣ እንዲህ ሆነ [ሀ]ሞሮኒ በህዝቡ መካከል ጦርነቱ፣ እናም ፀቡ እንዲቆ ምና፣ ህዝቡ ለሰላምና ለስልጣኔ ባስገደደ፣ እናም ከላማናውያን ጋር ለመዋጋት እንዲ ዘጋጁ ህጎችን ባዘጋጀ ጊዜ፣ እነሆ፣ ላማና ውያን በባህሩ ዳርቻ ወደሞሮኒ ምድር መጥ ተው ነበር።

፳፫ እናም እንዲህ ሆነ ኔፋውያን በሞ ሮኒ ከተማ በበቂ ሁኔታ ጠንካሮች አልነበ ሩም፤ ስለዚህ አማሊቅያ ብዙዎችን ኔፋው ያን በመግደል፣ እንዲሸሹ አደረገ። እናም እንዲህ ሆነ አማሊቅያ ከተማዋን፣ አዎን፣ ምሽጋቸውን በሙሉ ያዘ።

፳፬ እናም ከሞሮኒ ከተማ የሸሹት ወደ ኒፋአያህ ከተማ መጡ፤ እናም ደግሞ የሌሂ ከተማ ሰዎች እራሳቸውን በአንድ ላይ ሰበ ሰቡና፣ ዝግጅት አደረጉና፣ ላማናውያንን በጦርነት ለመቀበል እራሳቸውን አዘጋጅ ተው ነበር።

፳፭ ነገር ግን እንዲህ ሆነ አማሊቅያ ላማና ውያን በኒፋአያህ ከተማ ለመዋጋት እንዲ ሄዱ አልፈቀደላቸውም፣ ነገር ግን በባህሩ ዳርቻ እንዲቆዩ አደረገ፣ ሰዎችንም በሁ ሉም ከተማ በማድረግ ከተሞቹን እንዲከላ ከሉ እናም እንዲጠብቁ ተዋቸው።

፳፮ እናም የኒፋአያህን ከተማና፣ የሌሂን ከተማ፣ የሞሪያንተንንም ከተማ፣ የኦምነ ርን ከተማ፣ እናም የጊድን ከተማ፣ እንዲ ሁም የሙሌቅን ከተማ፣ ሁሉንም በባህሩ ዳርቻ በስተምስራቅ የሚገኙትን ከተሞች መያዙን ቀጠለ።

፳፯ እናም በአማሊቅያ ጮሌነት ላማና ውያን ቁጥር ስፍር በሌላቸው ሠራዊቶቻ ቸው፣ በሞሮኒ [ሀ]ምሽግ የተመሸጉትን ብዙ ከተሞችን አገኙ፤ እነዚህም በሙሉ ለላ ማናውያን ጠንካራ ስፍራዎችን ሰጣቸው።

፳፰ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን፣ ኔፋውያንን ከፊታቸው በማባረርና ብዙ ዎችን በመግደል ወደለጋስ ምድር ወሰን ዘመቱ።

፳፱ ነገር ግን እንዲህ ሆነ ሞሪያንተንን [ሀ]የገደለውን፣ እናም ህዝቡንም ከመሸሽ ካቆማቸው ከቴአንኩም ጋር ተገናኙ።

፴ እናም እንዲህ ሆነ፣ ከበርካታ ወታደ ሮቹ ጋር፣ የለጋስን ምድር፣ እናም ደግሞ በስተሰሜን በኩል ያለውን መሬት ለመ ውሰድ ወደፊት የተጓዘውን አማሊቅያንም ደግሞ አቆመው።

፴፩ ነገር ግን እነሆ በቴአንኩም እናም በእ ርሱ ሰዎች በመመለሱ፣ እነርሱም ታላቅ ጦረኞች በመሆናቸው ቁጣን አገኘ፤ ማን ኛውም የቴአንኩም ሰው የሆነ ላማናውያ ንን በብርታት እንዲሁም በጦር ስልት ስለ ሚበልጠው፣ ስለዚህም በላማናውያን ላይ የበላይነትን አገኙ።

፴፪ እናም እንዲህ ሆነ እነርሱም ጨለማ እስከሚሆን ድረስ አስፈራሩአቸውና ገደሉአቸው። እናም እንዲህ ሆነ ቴአን ኩምና፣ ሰዎቻቸው በለጋስ ምድር ዳርቻ ድንኳናቸውን ተከሉ፤ አማሊቅያም በባህሩ ዳር በኩል ባለው የባህር ዳርቻ በኩል ድንኳኑን ተከለና፣ በዚህም ሁኔታ ነበር የተባረሩት።

፴፫ እናም እንዲህ ሆነ ምሽት በሆነም ጊዜ፣ ቴአንኩምና አገልጋዩ በቀስታ በም ሽት ወጡ፣ ወደ አማሊቅያ የጦር ሰፈርም

፳ሀ አልማ ፵፮፥ ፲፪–፲፫።
፳፪ሀ ቅ.መ.መ. ሞሮኒ፣ ሻምበል።
፳፯ሀ አልማ ፵፰፥ ፰–፱።
፳፱ሀ አልማ ፶፥ ፴፭።

ሄዱ፤ እናም እነሆ፣ በስራቸውና በቀኑ ሙቀት የተነሳ እጅግ በመድከማቸው እን ቅልፍ ጥሏቸው ነበር።

፴፬ እናም እንዲህ ሆነ ቴአንኩም በቀስታ በድብቅ በመሆን ወደ ንጉሱ ድንኳን ገባና፣ በጦር ልቡን ወጋው፣ እናም እርሱም የን ጉሱ አገልጋዮች እንዳይነቁ ሞቱን በፍጥ ነት አደረገው።

፴፭ እናም ቴአንኩም በድጋሚ በሚስ ጥር ወደራሱ የጦር ሰፈር ተመለሰ፣ እናም እነሆ፣ ሰዎቹም ተኝተው ነበር፣ እርሱም ቀሰቀሳቸውና፣ ያደረጋቸውን ነገሮች በሙሉ ነገራቸው።

፴፮ እናም ላማናውያን ነቅተው በእነርሱ ላይ ይመጣሉ ብሎ በመፍራቱ ወታደሮቹ እንዲዘጋጁ አደረገ።

፴፯ እናም በኔፊ ህዝብ ላይ የመሣፍንቱ የሀያ አምስተኛ የንግስ ዘመን እንደዚህ ተፈ ፀመ፤ እናም የአማሊቅያ ዘመንም እንዲህ ተፈፀመ።

ምዕራፍ ፶፪

አሞሮን የላማናውያን ንጉስ በመሆን አማሊቅያን ተካው—ሞሮኒ፣ ቴአን ኩም፣ እናም ሌሂ ከላማናውያን ጋር ባደ ረጉት ጦርነት ኔፋውያንን በድል አድራ ጊነት መሩአቸው—የሙሌቅ ከተማ በድ ጋሚ ተወሰደች፣ እናም ዞራማዊው ያዕቆብ ተገደለ። ከ፳፯–፳፱ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም አሁን፣ እንዲህ ሆነ በኔፊ ህዝብ ላይ በመሣፍንቱ ሀያ ስድስተኛ የንግስ ዘመን፣ እነሆ፣ በመጀመሪያው ወር በጠዋት ላማናውያን ሲነቁ፣ እነሆ፣ አማሊቅያ በራሱ ድንኳን ውስጥ ሞቶ አገኙት፤ እናም ደግሞ በዚያን ቀን ቴአንኩም ከእነርሱ ጋር ለመዋ ጋት ዝግጁ መሆኑን ተመለከቱ።

፪ እናም እንግዲህ፣ ላማናውያን ይህንን በተመለከቱ ጊዜ ፈርተው ነበር፤ እናም ወደ ሰሜን ክፍል ለመዝመት ከነበራቸው ዕቅድ አንፃር ዕቅዳቸውን ተዉት፤ ከወታደሮቻ ቸው ጋርም ወደ ሙሌቅ ከተማ አፈገፈጉና፣ በምሽጋቸውም ጥበቃን ፈለጉ።

፫ እናም እንዲህ ሆነ የአማሊቅያ ወንድም በህዝቡ ላይ ንጉስ ሆኖ ተሾመ፤ እናም ስሙ አሞሮን ይባል ነበር፤ የአማሊቅያ ወንድም ንጉስ አሞሮን በአማሊቅያ ምትክ እንዲነ ግስ ተሹሞ ነበር።

፬ እናም እንዲህ ሆነ አሞሮን በደም መፋሰስ የተወሰዱትን ከተሞች ህዝቡ እን ዲቆጣጠር አዘዘ፣ የትኞቹንም ከተሞች ብዙ ደም ያለማፋሰስ አልወሰዱም ነበር።

፭ እናም እንግዲህ፣ ቴአንኩም ላማናው ያን የወሰዷቸውን ከተሞችና የያዟቸውን ቦታዎች ለመቆጣጠር ቆራጥ ውሳኔ አድ ርገው እንደነበር ተመለከተ፤ እናም ደግሞ ቴአንኩም በቁጥር እጅግ ብዙ መሆናቸውን በተመለከተ ጊዜ ላማናውያንን በምሽጋቸው ውስጥ እንዳሉ ለማጥቃት መሞከሩ አስፈ ላጊ አለመሆኑን አሰበ።

፮ ነገር ግን የእርሱ የሆኑትን ሰዎች ለጦ ርነት ያዘጋጀ በማስመሰል በዙሪያው እን ዲሆኑ አደረገ፤ አዎን፣ እናም በኔፋውያን ከተሞች ዙሪያ ግንብ ᐧገነባ፣ እናም ጠንካራ ስፍራን አዘጋጀ፣ ይህንንም ያደረገው በእ ርግጥ እራሱን ከእነርሱ ለመከላከል ነበር።

፯ እናም እንዲህ ሆነ ሞሮኒ ወታደሮቹን ለማጠናከር ብዙ ቁጥር ያላቸውን ሰዎች እስከሚልክ ድረስ ለጦርነት መዘጋጀቱን ቀጠለ።

፰ እናም ደግሞ ወደ እርሱ እጅ የገቡ ትን እስረኞችን በሙሉ እንዲጠብቁ ሞሮኒ መመሪያዎችን ላከ፤ ላማናውያን ብዙ እስረ ኞችን በመውሰዳቸው፣ ለወሰዱአቸው ማስ ለቀቂያ ይሆኑ ዘንድ የላማናውያን የሆኑትን እስረኞች እንዲጠብቁ ማድረግ ነበረበት።

፱ እናም ደግሞ የለጋስን ምድር እንዲ መሽጋት፣ እናም ላማናውያን ሥፍራዎቹን በመያዝ በሁሉም አቅጣጫ ለማጥቃት ኃይ ልን እንዳያገኙባቸው፣ ወደሰሜኑ በኩል የሚወስደውን ᐧቀጭኑን ጎዳና እንዲከላከል ትእዛዛትን ላከበት።

፶፪ ፲ᐧ አልማ ፶፡ ፩–፲፣ ፶፫፡ ፫–፰። ፱ᐧ አልማ ፳፪፡ ፴፪፣ ሞር. ፪፡ ፳፱።

፲ እናም ደግሞ ሞሮኒ ያለበትን ምድር በመከላከል ታማኝ እንዲሆን በመፈለጉና፣ በዚያች ምድር ላማናውያንን በሁሉም አጋጣሚ በስልጣኑ እስካለ ድረስ ለማጥቃትና፣ በተገኘው ሥልት ወይንም በሌላ መንገድ ከእጃቸው የወጡትን ከተሞች ዳግም ለመያዝ እድልን እንዲፈልግ፣ እናም ደግሞ በላማናውያን እጅ ያልወደቁትን በዙሪያው ያሉትን ከተሞች ምሽግ እንዲጠናክር ፈልጎት ነበር።

፲፩ እናም ደግሞ እንዲህ አለው፡ ወደ አንተ እመጣ ነበር፣ ነገር ግን እነሆ፣ ላማናውያን በባህሩ በስተምዕራብ በኩል ባለው ምድር ዳርቻ እየመጡብን ነው፤ እናም እነሆ፣ በእነርሱ ላይ እዘምታለሁ፣ ስለዚህ ወዳንተ ልመጣ አልችልም።

፲፪ እንግዲህ፣ ንጉሱ (አሞሮን) ከዛራሔምላ ምድር ወጣ፣ እናም ለንግስቲቱ የወንድሙን መሞት ነገራት፣ እናም ብዙ ሰዎችን በአንድነት ሰበሰበና፣ በባህሩ በስተምዕራብ ዳርቻም በኩል በኔፋውያን ላይ ዘመቱ።

፲፫ እናም ኔፋውያንን ለማጥቃትና ከባህሩ በስተምዕራብ ካለው ዳርቻም ኃይላቸውን እንዲያስወጡ ሞክሮ ነበር፤ እርሱ የወሰዳቸውን ከተሞች እንዲወርሱ የተዋቸውን በባህሩ በምስራቅ ዳርቻ በኩል ደግሞ ኔፋውያንን እንዲያጠቁአቸው፣ እናም እንደ ኃይላቸው፣ በሰራዊቶቻቸው ጉልበት መሰረት የእነርሱን ምድሮች እንዲወስዱም አዝዞአቸው ነበር።

፲፬ እናም በኔፊ ህዝብ ላይ በመሣፍንቱ ሀያ ስድስተኛ ዓመት ንገሳ መጨረሻ ላይ ኔፋውያን በእንዲህ ያለ አደገኛ ሁኔታ ላይ ነበሩ።

፲፭ ነገር ግን እነሆ፣ በመሣፍንቱ ሀያ ሰባተኛ ዓመት የንግስ ዘመን ቴአንኩም በሞሮኒ ትዕዛዝ፣ መርኒም የምድሪቱን ደቡብ፣ እና ምዕራብ ዳርቻዎች ለመጠበቅ ወታደሮችን በአቋቋመው፣ እናም ቴአንኩም ከህዝቡ ጋር የተቀማውን ከተሞች በድጋሚ ለማስመለስ ዘመቻውን ወደለጋስ ምድር አድርጎ ነበር፤

፲፮ እናም እንዲህ ሆነ ቴአንኩም በሙሌቅ ከተማ ላይ ጥቃትን ለማድረግ፣ እናም የሚቻል ከሆነ በድጋሚ ለመውሰድ ትዕዛዝ ተቀበለ።

፲፯ እናም እንዲህ ሆነ ቴአንኩም በሙሌቅ ከተማ ላይ ጥቃት ለማድረስ ተዘጋጀ፣ እናም በላማናውያን ላይ ከወታደሮቹ ጋር ለመዝመት ዝግጅት አደረገ፤ ነገር ግን በምሽጋቸው በነበሩበት ጊዜ እነርሱን ማሸነፍ የማይቻል መሆኑን ተመልክቶ ነበር፤ ስለዚህ ለወታደሮቹ ተጨማሪ ኃይልን ያገኝ ዘንድ የሞሮኒን መምጣት ለመጠበቅ ዕቅዱን ተወና፣ ወደለጋስ ከተማ በድጋሚ ተመለሰ።

፲፰ እናም እንዲህ ሆነ በኔፊ ህዝብ ላይ በመሣፍንቱ ሀያ ሰባተኛ ዓመት የንግስ ዘመን መጨረሻ ላይ ሞሮኒ ከሠራዊቱ ጋር በለጋስ ምድር ደረሰ።

፲፱ እናም በሀያ ስምንተኛው ዓመት መጀመሪያ፣ ሞሮኒና ቴአንኩም እናም በርካታ ዋና ሻምበሎች ስለጦርነቱ—ላማናውያን ከእነርሱ ጋር እንዲዋጉ ለማስወጣት፤ ወይም ኔፋውያን በጥቂት ዘዴዎች ላማናውያንን ከጠንካራው ምሽጋቸው እንዲያስወጡአቸው በድጋሚም በእነርሱ ላይ ኃይልን ያገኙ ዘንድ፣ እናም በድጋሚ የሙሌቅን ከተማ ለመውሰድ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ተማከሩ።

፳ እናም እንዲህ ሆነ የሙሌቅን ከተማ ወደሚጠብቁት የላማናውያን ሠራዊት መሪ ወደሆነው፣ ያዕቆብ ተብሎ ወደሚጠራው፣ ከሠራዊቱ ጋር በሁለቱ ከተሞች መካከል ባለው ባዶ ስፍራ እንዲገናኙ እንደሚፈልጉ መልዕክተኛ ላኩ። ነገር ግን እነሆ፣ ዞራማዊ የነበረው፣ ያዕቆብ፣ በገላጣው ስፍራ ከእነርሱ ጋር ለመገናኘት ከሠራዊቱ ጋር አልመጣም።

፳፩ እናም እንዲህ ሆነ በገላጣው ስፍራ ሞሮኒ እነርሱን እንደሚያገኛቸው ተስፋ ስላልነበረው፣ ስለዚህ፣ ላማናውያንን ከጠንካራው ምሽጋቸው ያወጣቸው ዘንድ አንድን ዕቅድ አዘጋጀ።

፳፪ ስለዚህ ቴአንኩም ጥቂት ቁጥር ያላ

ቸውን ሰዎች እንዲወስድ፣ እናም በባህሩ ዳርቻ አጠገብ እንዲዘምቱ አደረገ፤ እናም ሞሮኒና፣ ወታደሮቹ በምሽት በሙሌቅ ከተማ በስተምዕራብ በኩል ወደ ምድረበዳው ሄዱ፤ እናም በሚቀጥለው ቀን፣ የላማናውያን ጠባቂዎች ቴአንኩምን ባገኙት ጊዜ፣ ሮጡ፣ እናም ለመሪያቸው ለያዕቆብ ነገሩት።

፳፫ እናም እንዲህ ሆነ የላማናውያን ወታደሮች በቴአንኩም ላይ ዘመቱ፤ እናም በቁጥርም የቴአንኩም ሰዎችን በቁጥር ትንሽ ስለነበሩ እናሸንፋቸዋለን ብለው ገመቱ። እናም ቴአንኩም የላማናውያን ወታደሮች በእርሱ ላይ መምጣታቸውን በተመለከተ ጊዜ፣ በሰሜን በኩል በባህሩ ዳርቻ ማፈግፈግ ጀመረ።

፳፬ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን እርሱ መሸሹን በተመለከቱ ጊዜ፣ ድፍረትን አገኙና በወኔ ተከታተሉአቸው። እናም በከንቱ የተከተሉአቸውን ላማናውያን ቴአንኩም ባሳደዷቸው ጊዜ፣ እነሆ፣ ሞሮኒ ከእርሱም ጋር የነበሩት ሰራዊቶቹን እንዲዘምቱና ከተማዋን እንዲይዙ አዘዛቸው።

፳፭ እናም እንደዚህም አደረጉና፣ ከተማዋን ለመከላከል የቀሩትን፣ አዎን፣ ሁሉንም የጦር መሳሪያዎቻቸውን ያላስረከቡትን በሙሉ ገደሉአቸው።

፳፮ እናም ቴአንኩምን አሳደውት ከሚመለሱት ላማናውያን ጋር ለመገናኘት ከሚቀሩት ወታደሮች ጋር እየዘመተ እያለ፣ የሞሮኒ ሰራዊት ክፍል እንደዚህ የሙሌቅን ከተማ ያዙ።

፳፯ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን በለጋስ ምድር አጠገብ እስከሚመጡ ድረስ ቴአንኩምን ተከተሉት፣ እናም ከሌሂና ለጋስ ከተማን እንዲጠብቁ ከተተዉት ጥቂት ወታደሮች ጋር ተገናኙ።

፳፰ እናም አሁን እነሆ የላማናውያን የጦር አዛዥ ሌሂ ከወታደሮቹ ጋር ወደ እነርሱ መምጣታቸውን በተመለከተ ጊዜ፣ ሌሂ በእነርሱ ላይ ከመድረሱ በፊት የሙሌቅን ከተማ ለመያዝ አንችልም ብለው በመፍራታቸው በድንጋጤ ሸሹ፤ እነርሱም በጉዞአቸውም የተነሳ ደክመው ነበር፣ እናም የሌሂ ሰዎች ግን አልደከሙም ነበር።

፳፱ እንግዲህ ላማናውያን ሞሮኒ ከወታደሮቹ ጋር ከበስተጀርባቸው እንደሆነ አላወቁም ነበር፣ እናም ሁሉም የፈሩት ሌሂንና የእርሱን ህዝቦች ነበር።

፴ እንግዲህ ሌሂ ላማናውያንን ሞሮኒንና ወታደሮቹን እስከሚያገኙ ሊይዛቸው አልፈለገም ነበር።

፴፩ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን እርቀው ከማፈግፈጋቸው በፊት በኔፋውያን፣ በአንድ በኩል በሞሮኒ፣ እናም በሌላ በኩል በሌሂ ሰዎች ተከበው ነበር፤ ሁሉም ነቃ ያሉና በጥንካሬ የተሞሉ ነበሩ፤ ነገር ግን ላማናውያን ብዙ ስለተጓዙም ደክመው ነበር።

፴፪ እናም ሞሮኒ እነርሱ የጦር መሳሪያዎቻቸውን እስከሚያስረክቡ ድረስ ህዝቡ እንዲያጠቃቸው አዘዘ።

፴፫ እናም እንዲህ ሆነ፣ ያዕቆብ፣ መሪያቸው በመሆኑ፣ እንዲሁም ሠዖራማዊ በመሆኑ፣ እናም የማይሸነፍ መንፈስ ስለነበረው፣ ላማናውያን በኃይል ከሞሮኒ ጋር እንዲዋጉ መራቸው።

፴፬ ሞሮኒ ላማናውያን በሚጓዙበት አቅጣጫ ስለነበረ፣ ስለዚህም ያዕቆብ እነርሱን ለመግደል፣ እናም መንገዱን ወደ ሙሌቅ ከተማ ለመቁረጥ ወስኖ ነበር። ነገር ግን እነሆ፣ ሞሮኒና ህዝቡ እጅግ ኃይለኞች ነበሩ፤ ስለዚህ ከላማናውያን ፊት አላፈገፈጉም ነበር።

፴፭ እናም እንዲህ ሆነ ከሁለቱም በኩል እጅግ በኃይል ተዋጉ፤ እናም በሁለቱም በኩል ብዙዎች ሞቱ፤ አዎን እናም ሞሮኒ ቆስሎ ነበር፣ ያዕቆብም ተገድሎ ነበር።

፴፮ እናም ሌሂ በኃይል ከጠንካራዎቹ ህዝቦቹ ጋር ከጀርባቸው በሀይል አጥቅቷቸው፣ ላማናውያንም የጦር መሳሪያዎቻቸውን አስረከቡ፤ እናም የተቀሩት እጅግ

ግራ በመጋባታቸው ወዴት መሄድም፣ ሆነ እንዴት መዋጋት እንዳለባቸው አያውቁም ነበር።

፴፯ እንግዲህ ሞሮኒ ግራ መጋባታቸውን በተመለከተ ጊዜ፣ እንዲህ አላቸው፤ የጦር መሳሪያዎቻችሁን ወደዚህ ስፍራ የምታመጡ፣ እናም የምታስረክቡ ከሆነ፣ እነሆ ደማችሁን ማፍሰሳችንን እናቆማለን።

፴፰ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን ይህንን ንግግር በሰሙ ጊዜ፣ ዋና አዛዦቻቸው፣ ከሞት የተረፉት ሁሉ፣ ወደፊት በመምጣት በሞሮኒ እግር ስር የጦር መሳሪያዎቻቸውን ጣሉት፣ እናም ደግሞ ህዝቦቻቸውን በሙሉ እንደዚሁ እንዲያደርጉ አዘዙአቸው።

፴፱ ነገር ግን እነሆ፣ የጦር መሳሪያዎቻቸውን ያልጣሉ ብዙዎች ነበሩ፤ እናም ጎራዴዎቻቸውን ያልሰጡ ተወሰዱና፣ ታሰሩ፣ እናም የጦር መሳሪያዎቻቸውንም ተቀሙና፣ ከወንድሞቻቸው ጋር ወደ ለጋስ ምድር ለመሄድ ተገደዱ።

፴ እናም አሁን የተወሰዱት እስረኞች ከተገደሉት፣ አዎን፣ ከሁለቱም በኩል ከተገደሉት በቁጥር ይበልጡ ነበር።

ምዕራፍ ፶፫

የላማናውያን እስረኞች የለጋስን ምድር እንዲመሽጓት ጥቅም ላይ ውለዋል—በኔፋውያን መካከል የነበረው አለመስማማት ላማናውያን እንዲያሸንፉ አደረገ—ሔለማን በሁለት ሺህ የአምን ህዝብ ብላቴና ወንዶች ላይ ባለስልጣል ሆነ። ከ፳፰–፳፫ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ ኔፋውያን በላማናውያን እስረኞች ላይ ጠባቂዎችን አስቀመጡ፣ እናም እነርሱ እንዲሄዱና፣ የእራሳቸውን ሙታን፣ አዎን፣ እናም ደግሞ የተገደሉትን ኔፋውያንን እንዲቀብሩ አስገደዱአቸው፤ ሞሮኒም እነርሱ ስራቸውን በሚሰሩበት ጊዜ እንዲጠብቁአቸው ሰዎችን አስቀመጠ።

፪ እናም ሞሮኒ ከሌሂ ጋር ወደ ሙሌቅ ከተማ ሄደና፣ የከተማዋን ስልጣን ወሰደና ለሌሂ ሰጠው። እናም እነሆ፣ ይህ፣ ሌሂም፣ ከሞሮኒ ጋር በጦርነቱ በአብዛኛው ክፍል የነበረ ነው፤ እናም ሌሂ "እንደ ሞሮኒ ዓይነት ሰው ነበር፣ ሁለቱም ለየራሳቸው በሚያደርጉት ጥበቃ ተደሰቱ፤ አዎን፣ እርስ በእርስም ይዋደዱ ነበር፤ ደግሞም በኔፊ ህዝብ ሁሉ ይወደዱ ነበር።

፫ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን ከእነርሱ ወገን የሞቱትን፣ እናም ደግሞ ከኔፋውያን የሞቱትን ቀብረው ከጨረሱ በኋላ፤ ወደ ለጋስም ምድር ተመልሰው እንዲሄዱ ተደረጉ፤ እናም ቴአንኩም፣ በሞሮኒ ትዕዛዛት፣ እነርሱ ጉድጓዶችን በምድሪቱ ዙሪያ እንዲሁም በለጋስ ከተማ በመቆፈር ስራ እንዲጀምሩ አደረገ።

፬ እናም ለከተማዋ ቅርብ በሆነው ወንዝ ዳርቻ በጉድጓዱ በኩል ከእንጨት "አጥር እንዲሰሩ አደረገ፤ እናም በእንጨት በተሰራው አጥር ላይም ከጉድጓዱ አፈር በማውጣት አስቀመጡ፤ እናም እንደዚህ ላማናውያንን ለጋስን ምድርና ዙሪያውን በጠንካራ እንጨት አጥርና አፈር ትልቅ ከፍታም እንዲኖረው እስከሚያደርጉ ድረስ እንዲሰሩ አደረጓቸው።

፭ እናም ይህች ከተማም ከዚህም በኋላ እጅግ ጠንካራ ምሽግ ሆነች፤ በዚህችም ከተማ፣ አዎን፣ በራሳቸው እጅ እንዲሰሩ በአደረጉአቸው ግንብ ውስጥ የላማናውያን እስረኞችን ጠበቁ። እንግዲህ ላማናውያን እስረኞች በሚሰሩበት ወቅት መጠበቅ ቀላል በመሆኑ ሞሮኒ ላማናውያንን እንዲያሰራቸው ተገዶ ነበር፣ እናም በላማናውያን ላይ ጥቃት በሚያደርግ ጊዜ ጦሩ በሙሉ ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ ፈልጎ ነበር።

፮ እናም እንግዲህ ሞሮኒ ታላቅ ከሆኑት የላማናውያን ሠራዊቶች በአንዱ ላይ ድልን ተቀዳጅቶ ነበር፤ እናም በኔፊ ምድር የላማናውያን ጠንካራ ምሽግ የነበረውን የሙሌቅን ከተማ አግኝቷል፤ እናም እስ

ረኞችን ለመጠበቅም ደግሞ ጠንካራ ምሽግ
እንደዚህ ሰርቷል።
፯ እናም እንዲህ ሆነ በዚያን ዓመት ከላ
ማናውያን ጋር ጦርነትን አልሞከረም ነበር፤
ነገር ግን የራሱን ሰዎች ለጦርነት እንዲዘ
ጋጁ፤ አዎን፣ እናም ከላማናውያንም ለመ
ጠበቅ ምሽግን እንዲሰሩ፤ አዎን፣ እናም
ደግሞ ሴቶቻቸውና ልጆቻቸውን ከረሃብና
ከስቃይ እንዲወጡና፣ ለወታደሮቻቸው
ምግብ እንዲያገኙ አስደርጓል።
፰ እናም እንግዲህ እንዲህ ሆነ በባህሩ በስ
ተምዕራብ በደቡብ በኩል ሞሮኒ በሌለበት፣
በኔፋውያን መካከል በነበረው አለመስማ
ማት በመካከላቸው መለያየት እንዲፈጠር
በመደረጉ፣ አዎን፣ በዚያች ምድር ክፍል
የነበሩትን ከተሞች እስከሚያገኙ ድረስ የላ
ማናውያን ወታደሮች በኔፋውያን ላይ ጥቂት
ብልጫን አገኙ።
፱ እናም በመካከላቸው በነበረው ክፋት
የተነሳ፤ አዎን፣ በነበረው መለያየትና ሴራ
እጅግ አደገኛ በሆነ ሁኔታ ነበሩ።
፲ እናም አሁን እነሆ፣ በመጀመሪያ ላማና
ውያን ስለነበሩት *ሀ*የአሞን ሰዎች የምናገረው
አንድ ነገር አለኝ፤ ነገር ግን በአሞንና በወ
ንድሞቹ፣ ወይንም በእግዚአብሔር ቃልና
ኃይል፣ ወደ ጌታ *ለ*ተለውጠዋል፤ እናም
ወደ ዛራሔምላ ምድር ተወስደዋል፣ እና
በኔፋውያን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ተጠብቀ
ዋል።
፲፩ እናም በመሃላቸው ምክንያት በወ
ንድሞቻቸው ላይ የጦር መሳሪያዎቻቸ
ውን ከመውሰድ ተቆጥበዋል፤ ከዚህ በኋላ
በጭራሽ *ሀ*ደም ላለማፍሰስ መሃላን ሰጥ
ተው ነበር፤ እናም በመሀላቸው ምክንያት
ይጠፉም ነበር፤ አዎን፣ አሞንና ወንድሞቹ
ለህዝቡ ሩህሩህና ታላቅ ፍቅር ባይኖራቸው
ኖሮ እራሳቸውን በወንድሞቻቸው እጅ እን
ዲወድቁ ባደረጉነበር።
፲፪ እናም በዚህ የተነሳ ወደ ዛራሔምላ
ምድር ተወስደው ነበር፣ እናም በኔፋው
ያን ያለማቋረጥ *ሀ*ተጠበቁ።
፲፫ ነገር ግን እንዲህ ሆነ አደጋውንና፣
ስቃዩን፣ እናም ለእነርሱ ሲሉ ኔፋውያን
የደረሰባቸውን መከራ በተመለከቱ ጊዜ
አዘኑ፣ እናም ሀገራቸውን ለመከላከል
የጦር መሳሪያዎቻቸውን በማንሳት ለመ
ዋጋት *ሀ*ፈለጉ።
፲፬ ነገር ግን እነሆ፣ የጦር መሳሪያዎቻቸ
ውን ለማንሳት ሲሉም፣ በሔለማንና ወንድ
ሞቹ ማግባባት ተሸነፉ፣ ምክንያቱም የገቡ
ትን *ሀ*መሃላ *ለ*ለማፍረስ ተቃርበው ነበርና።
፲፭ እናም ሔለማን ይህንን በማድረጋቸው
ነፍሳቸውን ያጣሉ ብሎ ፈርቶ ነበር፤ ስለ
ዚህ ወደዚህ ቃል ኪዳን የገቡ ሁሉ በዚህ
ጊዜ በአደገኛው ሁኔታ ላይ ያሉትን የወ
ንድሞቻቸውን ስቃይ እንዲመለከቱ ተገ
ድደው ነበር።
፲፮ ነገር ግን እነሆ፣ እንዲህ ሆነ እነርሱ
ከጠላቶቻቸው ለመከላከል የጦር መሳሪያ
ዎቻቸውን ላለማንሳት ወደቃል ኪዳኑ ያል
ገቡ ብዙ ወንድ ልጆች ነበሯቸው፣ ስለዚህ
በዚህ ጊዜ የጦር መሳሪያዎቻቸውን ለማን
ሳት የሚችሉ ሁሉ እራሳቸውን ሰብስበው፣
እናም እራሳቸውን ኔፋውያን ብለው ጠሩ።
፲፯ እናም ለኔፋውያን ነፃነት ለመዋ
ጋት ቃል ኪዳን ገቡ፤ አዎን፣ ህይወታቸ
ውን እስከማጣት ድረስ ሀገራቸውን ለመ
ከላከል፤ አዎን፣ *ሀ*ነፃነታቸውን አሳልፈው
በጭራሽ እንደማይሰጡ፣ ነገር ግን በሁሉም
ሁኔታዎች ኔፋውያንን እናም እራሳቸውን
ከባርነት ለመከላከል እንደሚዋጉ ቃል ገብ
ተዋል።
፲፰ እናም እነሆ፣ ሁለት ሺህ የሚሆኑ
ወጣት ወንዶች ቃል ኪዳን ገብተዋል፣
እናም ሀገራቸውን ለመከላከል የጦር መሳ
ሪያዎቻቸውን አነሱ።
፲፱ እናም አሁን እነሆ፣ ከዚህ በፊት ኔፋ
ውያንን ፈፅሞ ጉዳት ያልነበሩ ቢሆኑም

፲ *ሀ* አልማ ፳፯፥ ፳፩–፳፮።
ለ አልማ ፳፫፥ ፰–፲፫።
፲፩ *ሀ* አልማ ፳፬፥ ፲፯–፲፱።
፲፪ *ሀ* አልማ ፳፯፥ ፳፫።
፲፫ *ሀ* አልማ ፶፮፥ ፯።
፲፬ *ሀ* ቅ.መ.መ. መሀላ።
ለ ዘኍል. ፴፥ ፪።
፲፯ *ሀ* አልማ ፶፮፥ ፵፯።
ቅ.መ.መ. መብት።

በዚህ ጊዜ ደግሞ ታላቅ ረዳት ሆኑላቸው፤ ምክንያቱም የጦር መሳሪያዎቻቸውን ወስ ደዋል፣ እናም ሔለማን መሪያቸው እንዲ ሆንም ፈልገዋል።

፳ እናም ሁሉም ወጣት ወንዶች ነበሩና፣ [ሀ]በድፍረትም፣ እናም ደግሞ በብርታትና በእንቅስቃሴአቸው በጣም ጀግኖች ነበሩ፤ ነገር ግን እነሆ ይህ ብቻም አልነበረም— በሁሉም ጊዜ በተሰጣቸው በማንኛውም ነገር [ለ]ታማኝ ሰዎች ነበሩ።

፳፩ አዎን የእውነት እና የጥሞና ሰዎች ነበሩ፣ ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ትዕ ዛዛት እንዲጠብቁና በፊቱም [ሀ]በቅንነት እን ደሚራመዱ ተምረዋልና።

፳፪ እናም አሁን እንዲህ ሆነ ሔለማን በምድሪቱ በደቡብ በባህሩ በምዕራብ በኩል ግንባር ያሉትን ሰዎች ለመርዳት [ሀ]ከሁለት ሺህዎቹን ብላቴና ሠራዊት በመምራት ዘመተ።

፳፫ እናም በኔፊ ህዝብ ላይ የመሣፍንቱ ሀያ ስምንተኛ የንግስና ዘመን ተፈፀመ።

ምዕራፍ ፶፫

አሞሮን እና ሞሮኒ እስረኞቻቸውን ለመ ለዋወጥ ተደራደሩ—ላማናውያን እን ዲወጡ እናም የሞት ጥቃታቸውን እን ዲያቆሙ ሞሮኒ ጠየቀ—አሞሮን ኔፋ ውያን የጦር መሳሪያቸውን እንዲጥሉ፣ እናም በላማናውያን ስር እንዲሆኑ ጠየቀ። በ፳፫ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም አሁን እንዲህ ሆነ በመሣፍንቱ ሀያ ዘጠነኛ ዓመት የንግስ ዘመን ውስጥ [ሀ]አሞሮን እስረኞችን ለመለዋወጥ በመፈ ለጉ ወደ ሞሮኒ መልዕክተኛን ላከ።

፪ እናም እንዲህ ሆነ ሞሮኒ ላማናውያንን ለመርዳት የቀረበውን ድጋፍ ለራሱ ህዝቦች ድጋፍ እንዲሆን በመፈለጉ በጥያቄው እጅግ ደስታ ተሰማው፤ እናም ደግሞ የራሱን ህዝብ ወታደሮቹን እንዲያጠናክሩለት ፈለገ።

፫ እንግዲህ ላማናውያን በርካታ ሴቶች ንና ልጆችን ማርከው ነበር፣ እናም ከሞሮኒ እስረኞች ውስጥ፣ ወይንም ሞሮኒ ከማረካ ቸው መካከል ምንም ሴትም ሆነ ልጅ አል ነበረም፤ ስለዚህ ሞሮኒ ከላማናውያን በሚ ቻለው ሁሉ የኔፋውያን እስረኞች የሆኑትን ብዙዎችን ለማግኘት በእርቅ ላይ ወሰነ።

፬ ስለዚህ ሞሮኒ ደብዳቤ ፃፈ፣ እናም በአሞሮን አገልጋይ ላከ፣ ይኸው አገል ጋይም ደብዳቤ ወደ ሞሮኒ አምጥቶ የነበ ረው ነው። እናም ለአሞሮን የፃፈው ቃል እንዲህ ይላል፥

፭ እነሆ፣ አሞሮን፣ በህዝቤ ላይ ያደረጋ ችሁትን፣ ወይንም የአንተ [ሀ]ወንድም በእ ነርሱ ላይ ያነሳውን፣ እናም ከሞተም በኋላ ጦርነቱን ለመቀጠል ስለወሰንከው ጦርነት በተመለከተ በመጠኑ ፅፌአለሁ።

፮ እነሆ፣ ንስሃ ካልገባችሁ፣ እናም ሠራ ዊቶቻችሁን ወደ ራሳችሁም ምድር ወይ ንም የኔፊ ምድር ወደሆነው ካልወሰዳችሁ በእናንተ ላይ ስለሚንዠበባለው ስለእግዚአ ብሔር [ሀ]ፍትህ እና የኃያሉ ጎራዴ ቁጣ በመ ጠኑ ልንገርህ።

፯ አዎን፣ ልትሰሟቸው የምትችሉ ቢሆን ኖሮ፣ እነዚህን ነገሮች እነግራችኋለሁ፤ አዎን፣ ንስሃ ካልገባችሁ እናም የመግደል ዓላማችሁን ካልተዋችሁ፣ እናም ወደራሳ ችሁ ምድር ከወታደሮቻችሁ ጋር ካልተ መለሳችሁ፣ እንደ አንተና ወንድምህ እን ደነበራችሁበት [ሀ]ግድያ ያደረጉትን ሊቀበላ ቸው ስለሚጠብቀው፣ አሰቃቂውን [ለ]ሲኦል በተመለከተ እነግራችኋለሁ።

፰ ነገር ግን አንዴ እነዚህን ነገሮች ስላ ልተቀበላችሁ፣ እናም ከጌታ ህዝብም ጋር ስለተዋጋችሁ፣ እንደዚሁ በድጋሚ እንደ ምታደርጉት እገምታለሁ።

፳ ሀ ቅ.መ.መ. መበርታት፣ ብርቱነት።
ለ ቅ.መ.መ. ቅንነት።
፳፩ ሀ ቅ.መ.መ. መራመድ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መራመድ (መሄድ)።
፳፪ ሀ አልማ ፶፤፡፣ ፲–፭።
፶፡ ፩ ሀ አልማ ፶፪፡፣ ፲።
፭ ሀ አልማ ፶፰፡፣ ፩።
፮ ሀ ቅ.መ.መ. ፍትህ።
፯ ሀ አልማ ፶፯፡፣ ፲፰፡ ፳፪–፳፬። ቅ.መ.መ. ግድያ።
ለ ቅ.መ.መ. ሲያል።

፱ እናም አሁን እነሆ፣ እናንተን ለመቀ
በል ተዘጋጅተናል፤ አዎን፣ እናም ያሰባ
ችሁትን ካልተዋችሁ፣ እነሆ የዚያን ያልተ
ቀበላችሁትን እግዚአብሔር ቁጣውን በራ
ሳችሁ ታደርጋላችሁ፣ እንዲሁም በፍጹም
እስክትጠፉ ድረስ።

፲ ነገር ግን ጌታ ህያው እንደሆነ እናንተ
ካልለቀቃችሁ በቀር ወታደሮቻችን በእ
ናንተ ላይ ይመጣሉ፣ እናም በቅርቡ ሞት
ይመጣባችኋል፣ ከተሞቻችንንና መሬታች
ንንም መልሰን እናገኛለንና፤ አዎን፣ እናም
ኃይማኖታችንንና የአምላካችንን ሁኔታ
እንጠብቃለን።

፲፩ ነገር ግን እነሆ፣ እነዚህን ነገሮች በተ
መለከተ በከንቱ የተናገርኩ ይመስለኛል፤
ወይንም አንተም [a]የሲኦል ልጅ እንደሆ
ንክ እገምታለሁ፣ ስለዚህ ለአንድ እስረኛ
የአንድን ሰው፣ ሚስቱንና ልጆቹን ካልለ
ቀቃችሁ በስተቀር፣ እስረኞችን አልለዋወ
ጥም፤ ይህንን የምታደርጉ ከሆነ እስረኞችን
እንለዋወጣለን።

፲፪ እናም እነሆ፣ ይህንን የማታደርጉ
ከሆነ፣ ከሠራዊቴ ጋር በእናንተ ላይ እመ
ጣባችኋለሁ፣ አዎን፣ ሴቶችና ልጆች ሳይ
ቀሩ አስታጥቃቸዋለሁ፣ እናም በእናንተ
ላይ እመጣባችኋለሁና፣ [a]የመጀመሪያው
የውርሳችን ምድር ወደሆነው ወደራሳችሁ
ምድር ድረስ እከተላችኋለሁ፤ አዎን፣
እናም ደም ለደም፣ አዎን፣ ህይወትም ለህ
ይወት ይሆናል፤ እናም ከምድር ገፅ እስከ
ምትጠፉም ድረስ እዋጋሀለሁ።

፲፫ እነሆ፣ እኔና ህዝቤ ተቆጥተናል፤ እኛን
ለመግደል ፈልጋችሁ ነበር፣ እናም እኛ
እራሳችንን ብቻ ለመከላከል ፈልገን ነበር።
ነገር ግን እነሆ፣ ከዚህ የበለጠም ልታጠፉን
ከፈለጋችሁ ልናጠፋችሁ እንፈልጋለን፤
አዎን፣ እናም የመጀመሪያው ውርሳችን
የሆነችውን ምድራችንንም እንፈልጋለን።

፲፬ አሁን ደብዳቤዬን እጨርሳለሁ። እኔ
ሞሮኒ ነኝ፣ የኔፋውያን ህዝብ መሪ ነኝ።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ አሞሮን ይህንን
ደብዳቤ በተቀበለ ጊዜ፣ ተቆጥቶ ነበር፤
እናም ለሞሮኒ ሌላ ደብዳቤ ፃፈ፣ እናም
የፃፈው ቃልም እንዲህ ይል ነበር፣

፲፮ እኔ የላማናውያን ንጉስ የሆንኩ አሞ
ሮን ነኝ፤ እናንተ [a]የገደላችሁት የአማሊቅያ
ወንድም ነኝ። እነሆ፣ ደሙን በእናንተ
እበቀላለሁ፣ አዎን፣ እናም ማስፈራሪያ
ችሁን ስለማልፈራ ከሠራዊቴ ጋር እመ
ጣባችኋለሁ።

፲፯ እነሆ፣ በትክክል ለእነርሱ የሆነውን
[a]የመንግስት መብታቸውን እስኪነጥቋቸው
ድረስ አባቶቻችሁ በወንድሞቻቸው ላይ
ግፍ ሰሩባቸው።

፲፰ እናም አሁን እነሆ፣ የጦር መሳሪያ
ዎቻችሁን የምትጥሉ ከሆነ፣ እናም መን
ግስት በትክክል ለሚገባቸው ራሳችሁን
የምታስገዙ ከሆነ፣ ህዝቤ የጦር መሳሪያ
ውን እንዲጥልና ከእንግዲህ እንዳይዋጋ
አደርጋለሁ።

፲፱ እነሆ፣ በእኔና በህዝቤ ላይ ብዙ የሚ
ያስፈሩ ንግግር ተናግራችኋል፤ ነገር ግን
እነሆ፣ ማስፈራሪያችሁን አልፈራነውም።

፳ ይሁን እንጂ፣ ለጦር ሰዎቼ ምግብ አስ
ቀምጥላቸው ዘንድ በጥያቄህ መሰረት በደ
ስታ እስረኞችን እቀያየራለሁ፤ እናም ኔፋ
ውያንን በእኛ አገዛዝ ስር ለማድረግ ወይንም
ለዘለዓለም እስከሚጠፉ ዘለዓለማዊ የሆነ
ጦርነት እናስነሳለን።

፳፩ እናም አልተቀበላችሁትም ያላችሁ
ትን እግዚአብሔር በተመለከተ፣ እነሆ፣
እንደዚህ ዓይነት ፍጡር አናውቅም፤ እና
ንተም አታውቁም፤ ነገር ግን እንደዚህ ዓይ
ነት ፍጡር ካለ አናውቀውም፣ ነገር ግን
እኛንም ሆነ እናንተን ፈጥሯል።

፳፪ እናም ዲያብሎስና ሲኦል ካለ እነሆ
እናንተ ከገደላችሁት እንደዚህ ወዳለው
ስፍራ ሄዷል ካላችሁበት ከወንድሜ ጋር
እንድትኖሩ አይልካችሁምን? ነገር ግን እነ
ዚህ ነገሮች ምንም አይደሉም።

---

[a] ሆ ዮሐ. ፰፡ ፵፪–፵፬።
[a] ፪ ኔፊ ፭፡ ፭–፰።
[a] ሆ ፪ አልማ ፶፭፡ ፴፬።
[a] ፪ ኔፊ ፭፡ ፩–፬፣
ሞዛያ ፲፡ ፲፪–፲፯።

፳፫ እኔ አሞሮን ነኝ፣ እናም አባቶቻ ችሁ ከኢየሩሳሌም እንዲወጣ ያስገደዱት ᵐየዞራም ወገን ነኝ።

፳፬ እናም እነሆ አሁን ደፋር ላማናዊ ነኝ፣ እነሆ ይህ ጦርነት የተደረገው ለተበደሉ በት ብቀላ ለማግኘትና፣ ለመንግስታቸው መብታቸውን ለመጠበቅና ለማግኘት ነው፤ እናም ለሞሮኒ የፃፍኩትን ደብዳቤ እደመ ድማለሁ።

ምዕራፍ ፶፭

ሞሮኒ እስረኞች መለዋወጥን ተቃወመ—የላማናውያን ጠባቂዎች በስካር ተጠመዱ፣ እናም ኔፋውያን እስረኞች ተለቀቁ—የጊድ ከተማም ያለደም መፋሰስ ተወሰደች። ከ፳፫–፳፪ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ ሞሮኒ ይህንን ደብ ዳቤ ሲቀበል ይበልጥ ተናደደ፣ ምክንያቱም አሞሮን ᵐያጭበርባሪነቱን ፍፁም እውቀት እንዳለው ያውቅ ስለነበር፤ አዎን፣ በኔፊ ህዝብ ላይ ለጦርነት ለመሰለፍ የተነሳሳ በት መንስኤው ትክክል እንዳልሆነ አሞ ሮን ማወቁን እርሱም ያውቃል።

፪ እናም እንዲህ አለ፥ እነሆ፣ በደብዳቤዬ እንደገለፅኩት ዓላማውን ካልቀየረ ከአሞ ሮን ጋር እስረኞች አልለዋወጥም፤ ምክን ያቱም ከነበረው የላቀ ኃይል እንዲኖረው አልፈቅድም።

፫ እነሆ፣ ላማናውያን የወሰዷቸውን እስ ረኞች የሚጠብቁበትን ስፍራ አውቃለሁ፤ እናም አሞሮን በደብዳቤዬ የጠየቅሁትን ስላልሰጠኝ እነሆ በቃሌ መሰረት አደርጋ ለሁ፤ አዎን በሞሮኒ ሰዎች መካከል ለሰ ላም አቤት እስከሚሉ ድረስ ሞትን እፈ ልጋለሁ።

፬ እናም አሁን እንዲህ ሆነ ሞሮኒ ይህ ንን ቃል በተናገረበት ጊዜ፣ በሞሮኒ ሰዎች መካከል የላማን ትውልድ የሆነ ሰው ምና ልባት ያገኘ ዘንድ በህዝቡ መካከል ፍተሻ እንዲሆን አደረገ።

፭ እናም እንዲህ ሆነ ላማን ተብሎ የሚ ጠራ አንድ ሰው አገኙ፤ እናም እርሱ በአ ማሊቅያ የተገደለው የንጉሱ ᵐአንድ አገል ጋይ ነበር።

፮ እናም ኔፋውያን እስረኞችን በሚጠ ብቁት ላይ ላማንና ቁጥር ያላቸው የእርሱ ሰዎች እንዲሄዱ ሞሮኒ አደረገ።

፯ አሁን ኔፋውያን በጊድ ከተማ ይጠበቁ ነበር፤ ስለዚህ ሞሮኒ ላማንን በመሾም እናም ጥቂት ቁጥር ያላቸው ሰዎችም ከእርሱ ጋር እንዲሄዱ አደረገ።

፰ እናም ምሽት በሆነ ጊዜ ላማን ኔፋው ያንን ወደሚጠብቁት ሄደ፣ እናም እነሆ፣ ሲመጣ ተመለከቱትና ጠሩት፤ ነገር ግን እንዲህ አላቸው፥ አትፍሩ፣ እነሆ፣ እኔ ላማናዊ ነኝ። እነሆ፣ ከኔፋውያን አምልጠ ናል፣ እነርሱም ተኝተዋል፤ እናም እነሆ ወይናቸውንም ወሰድንና ከእኛ ጋር አም ጥተናል።

፱ እናም ላማናውያን ይህንን ቃል በሰሙ ጊዜ በደስታ ተቀበሉት፤ እናም እንዲህ ሲሉ ተናገሩት፤ ወይኑን ይዘህ ስለመጣህ ተደስተናል፣ ደክሞናልና እንድንጠጣው ከወይኑ ስጠን።

፲ ነገር ግን ላማን እንዲህ አላቸው፥ ከኔ ፋውያን ጋር ለመዋጋት እስከምንሄድ ወይ ናችንን እናተርፍ። ነገር ግን ይህ አባባል በይበልጥ ከወይኑ ለመጠጣት እንዲፈልጉ አደረጋቸው።

፲፩ እንዲህም አሉ፥ እኛ ደክሞናል፣ ስለ ዚህ ከወይኑ እንውሰድ፣ እናም ከጥቂት ጊዜ በኋላ በኔፋውያን ላይ ለመሄድ ብርታት እን ዲሰጠን የወይኑ ድርሻችንን እንቀበላለን።

፲፪ እናም ላማን፣ እንደፍላጎታችሁ ልታ ደርጉ ትችላላችሁ አላቸው።

፲፫ እናም እንዲህ ሆነ ወይኑን በብዛት ጠጡ፤ ጣዕሙም አስደስቶአቸው ነበር፤ ስለዚህ ይበልጥ በብዛት ጠጡ፤ እናም የተ ዘጋጀውም ጠንካራ እንዲሆን ተብሎ ስለነ በር ኃይለኛ ነበር።

፲፬ እናም እንዲህ ሆነ ጠጡና፣ ተደሰቱ፣

እናም ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሁሉም ሰክረው ነበር።

፲፯ እናም እንግዲህ ላማንና የእርሱ የሆኑት ሁሉም መስከራቸውን፣ እናም ኃይለኛ እንቅልፍ እንደያዛቸው በተመለከቱ ጊዜ፣ ወደ ሞሮኒ ተመለሱና የሆነውን ነገር በሙሉ ነገሩት።

፲፰ እናም አሁን ይህ በሞሮኒ ዕቅድ መሰረት ነበር። እናም ሞሮኒ ተከታዮቹን በጦር መሳሪያዎች ትጥቅ አዘጋጃቸው፤ ላማናውያን ኃይለኛ እንቅልፍ በያዛቸውና በሰከሩ ጊዜ ወደ ጊድ ከተማ ሄዱ፣ እናም ሁሉም እስከሚታጠቁ ድረስም የጦር መሳሪያዎቻቸውን ለእስረኞቹ ወርውረው ሰጡአቸው፤

፲፱ አዎን፣ ሴቶቻቸውን፣ እናም ልጆቻቸውን በሙሉ ብዙዎች የጦር መሳሪያዎችን መጠቀም የሚችሉትን ሁሉ ሞሮኒ አስታጠቃቸው፤ እናም እነዚህ ነገሮች በሙሉ ፍፁም በሆነ ፀጥታ ነበር የተከናወኑት።

፲፳ ነገ ግን ላማናውያንን ቀስቅሰዋቸው ቢሆን ኖሮ፣ እነሆ ሰክረው ስለነበር፣ እናም ኔፋውያን ሊገድሉአቸው ይችሉ ነበር።

፲፱ ነገር ግን እነሆ፣ ይህ የሞሮኒ ፍላጎት አልነበረም፤ በግድያም ሆነ ᐪበደም መፋሰስ አይደሰትም ነበር፣ ነገር ግን ህዝቡን ከጥፋት በማዳን ይደሰታል፤ በዚህም የተነሳ በራሱ ላይ የግፍ ስራን አያመጣም፣ ላማናውያንን አያጠቃም፣ እናም በስካራቸው አያጠፋቸውም።

፳ ነገር ግን ፍላጎቱን ፈጸመ፤ በከተማዋ ግንብ ዙሪያ የነበሩትን ኔፋውያን እስረኞች አስታጥቆ ነበር እናም በግንቡ ውስጥ ያሉትን ሥፍራዎች እንዲወስዱ ኃይልን ሰጥቷቸው ነበር።

፳፩ እናም ከእርሱ ጋር የነበሩትን ሰዎች አንድ እርምጃ እንዲርቁ አደረገ፣ እናም የላማናውያንን ወታደሮች ከበቡአቸው።

፳፪ እናም እነሆ ይህ የተፈፀመውም በምሽት ነበር፣ ስለዚህ ላማናውያን ጠዋት ሲነቁ ከግንቡ በውጭ በኩል በኔፋውያን መከበባቸውን ተመለከቱ፣ እናም በውስጥ በኩል የነበሩት እስረኞቻቸውም ታጥቀው ከበዋቸው ነበር።

፳፫ እናም ላማናውያን በኔፋውያን ላይ ስልጣን እንደነበራቸውም ተመልክተው ነበር፤ እናም በዚህ ሁኔታ ከኔፋውያን ጋር መዋጋታቸው አስፈላጊ ሆኖ አላገኙትም ነበር፤ ስለዚህ ሊቀ ሻምባሎቻቸው የጦር መሳሪያዎቻቸውን ይፈልግ ነበር፣ እናም ወደፊት አመጡአቸውና፣ ምህረትን በመለመን በኔፋውያን እግር ስር ጣሉአቸው።

፳፬ እናም እነሆ፣ ይህ የሞሮኒ ፍላጎት ነበር። የጦር ምርኮኛ አድርጎ ወሰዳቸው፣ ከተማዋንም ያዘ፣ እናም ኔፋውያን የነበሩት እስረኞችን በሙሉ እንዲለቀቁ አደረገ፤ እናም እነርሱ ከሞሮኒ ወታደሮች ጋር ተቀላቀሉ፣ ለወታደሮቹም ታላቅ ድጋፍ ነበሩ።

፳፭ እናም እንዲህ ሆነ እስረኞች አድርጎ የወሰዳቸውን ላማናውያን በጊድ ከተማ ዙሪያ ያሉትን ምሽጎች ለማጠናከር ᐪስራ እንዲጀምሩ አደረገ።

፳፮ እናም እንዲህ ሆነ እንደፍላጎቱ የጊድን ከተማ ምሽግ ባደረገ ጊዜ፣ እስረኞቹ ወደ ለጋስ ምድር እንዲወሰዱ አድርጎ ነበር፤ እናም ደግሞ ከተማዋን እጅግ ታላቅ በሆነ ኃይል ያስጠብቅ ነበር።

፳፯ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን ይህንን ያህል ሴራ ቢያደርጉም ኔፋውያን የያዙአቸውን እስረኞች በሙሉ ጠበቁአቸው፣ እናም ደግሞ በድጋሚ ወስደውት የነበረውን ምድርና የበላይነታቸውን ተቆጣጠሩ።

፳፰ እናም እንዲህ ሆነ ኔፋውያን በድጋሚ ድል ማድረግ ጀመሩ፣ እናም ጥቅማቸውንና መብታቸውን ማስጠበቅ ጀመሩ።

፳፱ ብዙ ጊዜ ላማናውያን እነርሱን በምሽት ለመክበብ ይሞክሩ ነበር፣ ነገር ግን በዚህ ሙከራቸው ብዙ አስረኞቻቸውን አጥተዋል።

፴ እናም በስካር ወይንም በመርዝ ያጠፏቸው ዘንድ ለኔፋውያን ወይኖቻቸውን ሊሰጧቸው ብዙ ጊዜ ሞክረዋል።

፲፱ ᐪ አልማ ፴፭፡ ፲፯። ፳፭ ᐪ አልማ ፱፫፡ ፫–፭።

፴፩ ነገር ግን እነሆ፣ ኔፋውያን በስቃያቸው ጊዜ ጌታ አምላካቸውን ″ለማስታወስ የዘገዩ አልነበሩም። በእነርሱ ወጥመድም ሊያዙ አይችሉም ነበር፤ አዎን፣ ለጥቂት ላማና ውያን እስረኞች በቅድሚያ ካልሰጡ በቀር ከወይኑአቸው አይጠጡላቸውም ነበር።

፴፪ እናም በመካከላቸው መርዝ እንዳይሰ ጣቸው ይጠነቀቁ ነበር፤ ወይኑ ለላማናው ያን መርዝ ከሆነ ለኔፋውያንም መርዝ ይሆ ናልና፤ እናም መጠጦቻቸውን በሙሉ እን ደዚህ ቀመሱ።

፴፫ እናም እንግዲህ እንዲህ ሆነ የሞሪ ያንተንን ከተማ ለማጥቃት ሞሮኒ ዝግጅት ማድረጉ አስፈላጊ ነበር፤ እነሆም ላማና ውያን የሞሪያንተንን ከተማ እጅግ ጠንካራ እስከምትሆን ድረስ በድካማቸው መሽገዋ ታል።

፴፬ እናም ላማናውያን አዲስ ኃይል ወደ ከተማዋ፣ እናም ደግሞ አዳዲስ አቅርቦቶ ችን፣ ያለማቋረጥ ያመጡ ነበር።

፴፭ እናም በኔፊ ህዝብ ላይ የመሣፍንቱ ሀያ ዘጠነኛ የንግስ ዘመን ተፈፀመ።

ምዕራፍ ፶፰

ሔለማን ከላማናውያን ጋር የነበረውን ጦር ነት ሁኔታ በመዘርዘር ለሞሮኒ ደብዳቤ ላከ ለት—አንቲጱስ እና ሔለማን በላማናው ያን ላይ ታላቅ ድል አገኙ—የሔለማን ሁለት ሺህ ብላቴና ወንድ ልጆቹ በአስ ደናቂ ኃይል ተዋጉ፣ እናም ማናቸውም አልተገደሉም ነበር። ቁጥር ፩ በ፷፬ ም.ዓ. ገደማ፣ ከቁጥር ፪–፲፱ በ፷፫ ም.ዓ. ገደማ፤ እናም ከቁጥር ፳–፶፯ ከ፷፫–፷፪ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም አሁን እንዲህ ሆነ በመሣፍንቱ ሠላሳኛ ዓመት የንግስ ዘመን፣ በመጀመሪ ያው ወር በሁለተኛው ቀን፣ በዚያች ምድር ክፍል ያሉትን ሰዎች ሁኔታ የሚገልፅ ደብ ዳቤ ሞሮኒ ከሔለማን ተቀበለ።

፪ እናም የፃፋቸው ቃላት እንዲህ የሚሉ ነበሩ፥ በጌታ እንዲሁም በጦርነቱ ወቅት በመከራው ጊዜ የተወደድክ ውድ ወን ድሜ፣ ሞሮኒ፣ እነሆ፣ የተወደድክ ወን ድሜ፣ በዚህች ምድር ጦርነታችንን በሚ መለከት በመጠኑ የምነግርህ አለኝ።

፫ እነሆ አሞን ከኔፊ ምድር ያመጣቸው እነዚያ ሰዎች ″ሁለት ሺህ ወንድ ልጆች—አሁን እነዚህ የአባታችን የሌሂ ትልቅ ልጅ የላማን ዘርያዎች እንደሆኑ ታውቃለህ፤

፬ አሁንም እነዚህን ነገሮች ሁሉ በተመለ ከተ ስለምታውቅ ስለወጋቸውም ሆነ ስለአ ለማመናቸው አልነግርህም—

፭ ስለዚህ እነዚህ ሁለት ሺህ ወጣት ሰዎች የጦር መሳሪያዎቻቸውን እንዳነሱ እናም መሪያቸው እንድሆን መፈለጋቸውን መና ገር ይበቃኛል፤ እናም እኛ ሀገራችንን ለመ ከላከል ወደፊት መጥተናል።

፮ እናም አሁን ደግሞ በወንድሞቻቸው ላይ ደም ለማፍሰስ የጦር መሳሪያዎቻቸ ውን ላለማንሳት አባቶቻቸው የገቡትን ″ቃል ኪዳን በተመለከተ ታውቃለህ።

፯ ነገር ግን በሀያ ስድስተኛው ዓመት፣ ለእነርሱ የነበረንን ስቃያችንንና መከራችንን በተመለከቱ ጊዜ፣ ቃል ኪዳናቸውን ″ለማ ፍረስ እናም እኛን ለመከላከል የጦር መሳ ሪያዎቻቸውን ለማንሳት ተቃርበው ነበር።

፰ ነገር ግን በወሰዱት ቃል ኪዳን መሟ ላት መንስኤ በተጨማሪ እንዳንሰቃይ በመ ፍቀድ እግዚአብሔር ያበረታናል ብዬ በመ ገመቴ፣ ይህን የገቡትን መሃላ እንዲያፈርሱ አልፈቀድም።

፱ ነገር ግን እነሆ፣ ደስታ የምናገኝበት አንድ ነገር ይህ ነው። እነሆም፣ በሀያ ስድ ስተኛው ዓመት፣ እኔ ሔለማን፣ የዚያች ምድር መሪ አድርገህ የሾምከውን አን ቲጱስን ለመርዳት ወደ ይሁዳ ከተማ እነ ዚህን ሁለት ሺህ ወጣት ሰዎች በመምራት ዘመትኩ።

፲ እናም ሁለት ሺህ ልጆቼን (ልጆች

፴፩ ሀ አልማ ፳፪ ፥ ፴፪–፴፬።
፶፰ ፫ ሀ አልማ ፶፫ ፥ ፳፪።
፮ ሀ አልማ ፳፬ ፥ ፲፯–፲፰።
፯ ሀ አልማ ፶፫ ፥ ፲፫–፲፭።

ተብሎ ለመጠራት ብቁ ነበሩና) ከአንቲጹስ ሠራዊት ጋር ቀላቀልኳቸው፣ በዚህም ኃይል አንቲጹስ እጅግ ተደስቶ ነበር፤ እነ ሆም፣ የእርሱ ሠራዊት በላማናውያን ተቀ ንሰው ነበር፣ ምክንያቱም የእነርሱ ኃይል ትልቅ ቁጥር ያለውን ህዝባችንን ገደለውብ ናልና፣ ለዚህ እንድናዝንም አድርጎን ነበር።

፲፩ ይሁን እንጂ በዚህ ነጥብም እራሳችንን እናፅናናለን፣ እነርሱ የሞቱት ለሀገራቸው፣ እናም ለአምላካቸው መንስኤ ነው፣ አዎን እናም እነርሱ ᐟደስተኞች ናቸው።

፲፪ እናም ላማናውያን ደግሞ ብዙ እስረኞ ችን ያዙ፣ ሁሉም ዋና አዛዦች ነበሩ፣ ሌሎ ቹን በህይወት አላተረፉአቸውም ነበር። እናም እነርሱ በዚህን ጊዜ በኔፊ ምድር ነበሩ ብለን እንገምታለን፤ ካልተገደሉ ይህ ነበር ሁኔታው።

፲፫ እናም አሁን የጀግኖቻችንን ደም በማ ፍሰስ ላማናውያን ያገኙአቸው ከተሞች እነ ዚህ ናቸው፥

፲፬ የማንቲ ምድር፣ ወይንም የማንቲ ከተ ማና፣ የዚኤዝሮም ከተማ፣ እናም የቁሜኒ ከተማና፣ የአንቲፓራ ከተማ።

፲፭ እኔ በይሁዳ ከተማ ስደርስ በላማና ውያን የተያዙት ከተሞች እነዚህ ናቸው፤ እናም አንቲጹስና የእርሱ የሆኑት በጉል በታቸው ከተማውን ምሽግ ለማድረግ ሲደክሙ አገኘኋቸው።

፲፮ አዎን፣ እናም ከተማቸውን ለመጠበቅ ሲሉ በቀን በጀግንነት በመዋጋታቸው በም ሽትም በድካም ስለሰሩ ሰውነታቸው እንዲ ሁም መንፈሳቸው ደክሞ ነበር፤ እናም በሁ ሉም ዓይነት ታላቅ ስቃይ እንደዚህ ተሰቃ ይተዋል።

፲፯ እናም አሁን እነርሱ በዚህች ስፍራ ለማሸነፍ ወይንም ለመሞት ቆርጠው ነበር፤ ስለዚህ ይህችን ከእኔ ጋር ያመ ጣኋት ትንሽ ኃይል፣ አዎን የእኔም ልጆች፣ ታላቅ ተስፋንና ብዙ ደስታን እንደሰጡአ ቸው በሚገባ ልትገምት ትችላለህ።

፲፰ እናም አሁን እንዲህ ሆነ ላማናውያን የአንቲጹስ በወታደሮቹ ታላቅ ብርታትን መቀበሉን በተመለከቱ ጊዜ ለውጊያ በይ ሁዳ ከተማም ላይ ወይንም በእኛ ላይ በድ ጋሚ እንዳይመጡ በአሞሮን ትዕዛዛት ተገ ደዱ።

፲፱ እናም በጌታ እንደዚህ ተወድደን ነበር፤ በድካማችን ላይ ምናልባት ቢመጡ በቁጥር ትንሽ በሆኑት ወታደሮቻችን ባጠፏቸው ነበር። ነገር ግን እኛ እንደዚህ ተጠብቀን ነበር።

፳ እነርሱም የወሰዱአቸውን ከተሞች እንዲያስተዳድሩ በአሞሮን ታዘው ነበር። እናም ሀያ ስድስተኛው ዓመት እንደዚህ ተፈፀመ። እናም በሀያ ሰባተኛው ዓመት መጀመሪያ ከተማችንንና እራሳችንን ለመ ከላከል አዘጋጀን።

፳፩ እንግዲህ ላማናውያን ወደእኛ እንዲ መጡ ፈልገን ነበር፤ ምክንያቱም በጠንካ ራው ምሽጋቸው ጥቃት ለማድረግ አልፈ ለግንም ነበርና።

፳፪ እናም እንዲህ ሆነ በስተሰሜን በኩል የሚገኙትን ሌሎች ከተሞቻችንን በምሽ ትም ሆነ በቀን ላማናውያን አልፈው እን ዳያጠቁን እንቅስቃሴአቸውን ለመቆጣጠር በዙሪያችን ሰላዮችን አስቀምጠን ነበር።

፳፫ በከተሞቹም እነርሱን ለመቋቋም በበቂ ሁኔታ ጠንካሮች እንዳልነበሩ እናውቅ ነበርና፤ ስለዚህ እኛን የሚያልፉ ከሆነ ከጀ ርባቸው ለማጥቃት እናም በተመሳሳዩ ጊዜ በግንባር ከእነርሱ ጋር ከጀርባቸው ለመገና ኘት ፈልገን ነበር። ልናሸንፋቸው እንችላ ለን ብለንም ገምተን ነበር፤ ነገር ግን እነሆ፣ በዚህም ፍላጎቶቻችን ተበሳጭተን ነበር።

፳፬ በቂ ብርታት ሳይኖራቸው እንሸነፋለን ብለው በመፍራታቸው፣ ከሙሉ ወታደሮ ቻቸው ጋርም ይሁን ከጥቂቶች አልፈውን ለመሄድ አልደፈሩም ነበር።

፳፭ በዛራሔምላ ከተማም ላይ ቢሆን ለመዝመት አልደፈሩም ነበር፤ በኔፊሃያም ከተማ ላይ የሲዶምን ምንጭ ለማቋረጥ አልደፈሩም ነበር።

፲፩ ᐟ አልማ ፳፯፡፲፪።

፳፮ እናም በነበራቸው ኃይል የወሰዱአ ቸውን ከተሞች ለመጠበቅ ወስነው ነበር።

፳፯ እናም እንግዲህ እንዲህ ሆነ በዚህ ዓመት በሁለተኛው ወር፣ ከሁለት ሺህ ልጆቻችን አባቶች ብዙ ስንቆች መጥተ ውልን ነበር።

፳፰ እናም ደግሞ ከዛራሔምላ ምድር ሁለት ሺህ ሰዎች ወደ እኛ ተልከው ነበር። እናም ከአስር ሺዎቹ ሰዎች ጋርና፣ ለእነ ርሱ፣ እናም ደግሞ ለሚስቶቻቸውና ለል ጆቻቸው ስንቅ አዘጋጅተን ነበር።

፳፱ እናም ላማናውያን ኃይላችን ቀን በቀን መጨመሩንና፣ ለድጋፋችን ስንቅ እንደደረሰን በመመልከታቸው፣ መፍራት ጀመሩ፣ እናም ስንቅና ሀይል መቀበላች ንን ማቆም የሚቻላቸውም ቢሆን ተመኝ ተው ለጥቃት ገሰገሱ።

፴ እንግዲህ በዚህ መንገድ ላማናው ያን መጨነቅ መጀመራቸውን በምንመ ለከትበት ጊዜ፣ አንድን ዕቅድ በእነርሱ ላይ ተግባራዊ ለማድረግ ፈለግን፤ ስለ ዚህ አንቲጹስ ከትናንሽ ልጆቼ ጋር ወደ ጎረቤት ከተማ ልክ ወደ ጎረቤት ከተሞች ስንቅ የምንወስደው ያለ በማስመሰል እን ድዘምት አዘዘኝ።

፴፩ እናም በባህሩ ዳርቻ ከከተማዋ ርቀን የሄድን በመምሰል ወደ አንቲፓራ ከተማ አጠገብ ዘምተን ነበር።

፴፪ እናም እንዲህ ሆነ፣ ስንቃችንን የያ ዝን በመምሰል ወደዚያች ከተማ ለመጓዝ ወደፊት ዘመትን።

፴፫ እናም እንዲህ ሆነ አንቲጹስ የወታ ደሮቹን ክፍል በመያዝ የተቀሩትን ከተማ ዋን እንዲጠብቁ በማድረግ ሄደ። ነገር ግን ከጥቂት ወታደሮቹ ጋር ወደፊት እስከምሄድ እናም በአንቲፓራ ከተማ አጠገብ እስከመ ጣሁ ድረስ አልዘመተም ነበር።

፴፬ እናም አሁን፣ በአንቲፓራ ከተማ የላማናውያን ጠንካራ ወታደሮች ሰፍረው ነበር፤ አዎን፣ በቁጥርም እጅግ ብዙ ነበሩ።

፴፭ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን በሰ ላዮቻቸው በተነገራቸው ጊዜ፣ ከወታደሮ ቻቸው ጋር በመሆን ወደፊት መጡና በእኛ ላይ ዘመቱ።

፴፮ እናም እንዲህ ሆነ ከፊታቸው በሰሜን በኩል ሸሸን። እናም ጠንካራ የነበሩትን የላ ማናውያን ሠራዊት እንደዚህ በመምራት ከእዚያ አስወጣናቸው፤

፴፯ አዎን፣ የአንቲጹስ ወታደሮች በኃ ይል እንዳባረሩአቸው በተመለከቱ ጊዜ፣ ወደቀኝም ሆነ ወደግራው እስከማይመ ለሱበት፣ ነገር ግን ጉዞአቸውን ከኋላችን እኛን በቀጥታ እየተከተሉእስከሚቀጥሉበት በብዙ ርቀትም መራናቸው፤ እናም፣ አን ቲጹስ እነርሱ ላይ ከመድረሱ በፊት ዓላማ ቸው እኛን ለመግደል እንደነበር ገመትን፣ እናም ይህም የሆነው በህዝባችን እንዳይከ በቡ ነበር።

፴፰ እናም እንግዲህ አንቲጹስ አደጋ ላይ መሆናችንን በተመለከተ ጊዜ፣ የወታደሮ ቹን ጉዞ አፋጠነው። ነገር ግን እነሆ፣ ምሽት ነበር፣ ስለዚህ እኛን አልደረሱብንም፣ አን ቲጹስም ቢሆን አልደረሰባቸውም፤ ስለዚህ በምሽት ሰፈርን።

፴፱ እናም እንዲህ ሆነ ከመንጋቱ በፊት፣ እነሆ፣ ላማናውያን ያሳድዱን ነበር። አሁን ከእነርሱ ጋር ለመዋጋት በብቃት ጠን ካራ አልነበረንም፤ አዎን፣ ትንሾቹ ወንድ ልጆቼ በእጃቸው እንዲወድቁ አልፈቅ ድም፣ ስለዚህ ጉዞአችንን ቀጠልን፣ እናም ጉዞአችንን ወደ ምድረበዳው አደረግን።

፵ እንግዲህ እነርሱ እንከበባለን ብለው በመፍራታቸው ወደቀኝም ሆነ ወደግራ ለመዞር አልደፈሩም ነበር፤ ያጠቁኛል ብዬ በመፍራቴ እኔም ወደቀኝም ሆነ ወደግራ አልዞርኩም፣ እናም ጥቃታቸውንም ለመ ቋቋም አንችልም ነበር፤ ነገር ግን እንገደላ ለንና እነርሱም ያመልጣሉ፤ እናም ምሽት እስከሚሆንም ድረስ ወደ ምድረበዳው ቀኑን በሙሉ ሸሸን።

፵፩ እናም በድጋሚ እንዲህ ሆነ፣ የጠዋት ፀሀይ በእኛ ላይ ስትሆን፣ ላማናውያን እኛን መቅረባቸውን ተመለከትን፣ እናም ሸሸን።

፵፪ ነገር ግን እንዲህ ሆነ፣ ከመቆማቸው

በፊት በርቀት አልተከታተሉንም ነበር፣ እናም ይህ የነበረው በሰባተኛው ወር በሶ ስተኛው ቀን ጠዋት ነበር።

፶፣ እናም አሁን፣ አንቲጹስ እንደደረሰ ባቸው አናውቅም ነበር፣ ነገር ግን ለሰዎቹ እንዲህ አልኩ፡ እነሆ፣ በወጥመዳቸው እስ ከሚይዙን ድረስ ወደ እነርሱም እንድን መጣ ዘንድ ቆመው እንደሆነ አናውቅም፤

፶፪ ስለዚህ ልጆቼ ምን ትላላችሁ፣ እነር ሱን ለመዋጋት ትሄዳላችሁን?

፶፫ እናም አሁን እንዲህ እልሃለሁ፡ የተ ወደድክ ወንድሜ ሞሮኒ፣ እንዲህ ያለን ታላቅ ᐟᐟድፍረትን በጭራሽ በኔፋውያን ሁሉ መካከል አላየሁም።

፶፤ ሁልጊዜም ልጆቼ ብዬ እንደምጠራ ቸው (ሁሉም ወጣቶች ናቸውና) እነርሱም እንዲህ አሉኝ፡ አባታችን፣ እነሆ አምላካ ችን ከእኛ ጋር ነው፤ እናም እንድንወድቅ አይፈቅድም፤ እንሂድ፤ ብቻችንን የሚ ተዉን ከሆነ ወንድሞቻችንን አንግድልም ነበር፤ ስለዚህ የአንቲጹስን ሠራዊት እን ዳያሸንፉ ዘንድ እንሂድ።

፶፣ እንግዲህ ፈፅሞ ተዋግተውም አያ ውቁም፤ ይሁን እንጂ ሞትን አይፈሩም ነበር፤ እናም ከህይወታቸው የበለጠ ለአ ባቶቻቸው ᐟᐟነፃነት በይበልጥ ያስቡ ነበር፤ አዎን፣ ጥርጣሬ ከሌለባቸው እግዚአብ ሔር እንደሚጠብቃቸው ᐟᐟበእናቶቻቸ ውም ተምረዋል።

፶፣ እናም እናቶቻቸው የተናገሩትን ቃላት እንዲህ ሲሉም ነገሩኝ፡ እናቶቻች ንም ይህን እንደሚያውቁት ጥርጣሬ የለ ንም።

፶፪ እናም እንዲህ ሆነ እኛን ይከታተሉን ወደነበሩት ላማናውያን ከሁለት ሺህዎቹ ጋር ተመለስኩ። እናም አሁን እነሆ፣ የአን ቲጹስ ሠራዊት ደርሰውባቸው ነበር፤ እናም አሰቃቂው ጦርነት ተጀምሮ ነበር።

፶ የአንቲጹስ ሠራዊት በዚያች በትንሽ ጊዜ ረጅም ጉዞ ተጉዘው በመድከማቸው በላማናውያን እጅ ለመውደቅ ተቃርበው ነበር፤ እናም ከሁለት ሺህዎቹ ጋር ባልመ ለስ ኖሮ ያሰቡት ይሳካላቸው ነበር።

፶፩ በጉዞአቸው ፍጥነት በመድከማቸው፣ አንቲጹስ፣ እናም ብዙዎቹ የእርሱ መሪዎች በጎራዴ ወድቀው ነበር—ስለዚህ መሪዎ ቻቸው ስለወደቁባቸው የአንቲጹስ ሰዎች በመረበሻቸው ከላማናውያን ፊት ማፈግፈ ጀምረው ነበር።

፶፪ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን በረ ቱና፣ እነርሱን ማሳደድ ጀመሩ፤ እናም ሔለማን ከሁለት ሺህዎቹ ጋር ወደእነርሱ በመጣና በእጅ ይገድሏቸው በጀመሩ ጊዜ ላማናውያን በታላቅ ኃይል እየተከተሏቸው ነበር፣ እናም የላማናውያን ሠራዊት በሔለ ማን ላይ እስከሚመለሱ ድረስ ያጠቋቸው ጀመር።

፶፣ እናም የአንቲጹስ ሰዎች ላማናውያን መመለሳቸውን በተመለከቱ ጊዜ፣ ህዝባቸ ውን በአንድ ላይ ሰበሰቡና፣ እንደገና በላ ማናውያን ጀርባ ላይ መጡባቸው።

፶፩ እናም እንግዲህ እንዲህ ሆነ እኛ የኔፊ ህዝብ፣ የአንቲጹስ ህዝብና እኔ ከሁለት ሺህዎቹ ጋር ላማናውያንን ከበብንና፣ ገደ ልናቸው፤ አዎን፣ የጦር መሳሪያዎቻቸውን እስከሚያስረክቡ፣ እናም ደግሞ እራሳቸ ውን የጦር ምርኮኛ እስከሚያደርጉ ድረስ ተገደሉ።

፶፣ እናም እንግዲህ እንዲህ ሆነ በእ ኛም ሙሉ በሙሉ በምርኮ ከተያዙ በኋላ፣ እነሆ፣ ብዙ ወጣቶች ተገድለዋል ብዬ በመ ፍራቴ ከእኔ ጋር የተዋጉትን ወጣቶች ቆጠ ርኳቸው።

፶፤ እናም እነሆ፣ ለእኔ ታላቅ ደስታ የሆ ነው ከእነርሱ ᐟᐟአንዲትም ነፍስ መሬት ባለ መውደቋ ነበር፤ አዎን፣ በእግዚአብሔርም ጥንካሬ እንደተዋጉ ያህል ነበር፤ አዎን፣ ሰው በጭራሽ በእንደዚህ ዓይነት ታምራዊ በሆነ ጉልበት ተዋግቶ አይታወቅም ነበር፤ እናም በአስገራሚ ኃይል በላማናውያን ላይ

ᐟᐟ ᐟᐟ ᐟᐟ

ᐟᐟ ᐟᐟ ᐟᐟ

ᐟᐟ ᐟᐟ ᐟᐟ

ስለወደቁ፣ አስፈርተዋቸውም ነበር፤ በዚ
ህም የተነሳ ላማናውያን እራሳቸውን የጦር
ምርኮኛ አድርገው ሰጡ።

፶፯ እናም፣ ከላማናውያን ወታደሮች እን
ጠብቃቸው ዘንድ ለእስረኞቻችን ቦታ ስለ
ሌለን፤ ስለዚህ ወደ ዛራሔምላ ምድር ላክ
ናቸው፤ ያልሞቱትን የአንቲጹስ ሰዎችንም
ከእነርሱ ጋር ልከናቸዋል፤ እናም የተቀሩ
ትን ወስጺ ከብላቴና ᵘአሞናውያን ጋር አደ
ባለቅሁአቸው፤ ጉዞአችንንም ወደ ይሁዳ
ከተማ አደረግን።

ምዕራፍ ፶፯

*ሔለማን የአንቲፓራን መያዝ፣ እናም
የቁሜኒ ከተማን መከበብና፣ መከላከል
በተመለከተ በዝርዝር አወራ—ወጣት
አሞናውያኑ በጀግንነት ተዋጉ፤ ሁሉም
ቆሰሉ፣ ነገር ግን አንድም አልተገደለም—
ጌድ የላማናውያን እስረኞችን ሞትና ማም
ለጥ ሀተታ አቀረበ። በ፳፫ ም.ዓ. ገደማ።*

፩ እናም እንዲህ ሆነ ከንጉስ፣ አሞሮን፣
የጦር ምርኮኞቹን የምንለቅለት ከሆነ የአ
ንቲፓራ ከተማ እንደሚለቅልኝ የሚገልፅ
ደብዳቤ ደረሰኝ።

፪ ነገር ግን ባሉን ወታደሮች የአንቲፓራን
ከተማ ለመውሰድ እርግጠኞች እንደሆንን፣
እናም ለከተማዋ ሲባል እስረኞችን በመለ
ዋወጥ እራሳችንን እንደ ሞኝ መገመት እን
ደሚገባንና፣ እስረኞቻችንን በመለዋወጥ
ብቻ ነው እንደምንለቃቸው ለንጉሱ ደብ
ዳቤ ላክኩለት።

፫ እናም አሞሮን እስረኞችን ስለማይቀ
ያየር ደብዳቤዬን አልተቀበለውም፤ ስለ
ዚህ ወደ አንቲፓራ ከተማ ለመሄድ ዝግ
ጅት ማድረግ ጀመርን።

፬ ነገር ግን የአንቲፓራ ከተማ ህዝብ ከተ
ማዋን ትተው ሄዱ፣ እናም ወደ ሌለኛው
የያዙአቸው ከተማቸው ለመመሸግ ሸሹ፤
እናም የአንቲፓራ ከተማ በእጃችን ወደ
ቀች።

፭ እናም የመሣፍንቱ ሀያ ስምንተኛ ዓመት
የንግስ ዘመን እንደዚህ ተፈፀመ።

፮ እናም እንዲህ ሆነ በሀያ ዘጠነኛው
ዓመት መጀመሪያ ቀለብ ተቀበልን፣ እናም
ደግሞ ከዛራሔምላ ምድር ለወታደሮቻችን
ተጨማሪ ኃይልና በዙሪያውም ካሉት ሀገ
ሮች ስድስት ሺህ ሰዎችን፣ ከዚህ በተጨ
ማሪ ስልሳ ᵘአሞናውያን ልጆች ከእኔ ትን
ንሾች ሁለት ሺህ ክምችቶች ወንድሞቻ
ቸው ጋር ለመቀላቀል መጡ። እናም አሁን
እነሆ፣ እኛ ጠንካሮች ነበርን፤ አዎን፣ እናም
ደግሞ በርካታ ቀለብ መጥተውልን ነበር።

፯ እናም እንዲህ ሆነ የቁሜኒን ከተማ
ለመከላከል ከተቀመጡት ሠራዊት ጋር
ውጊያ ማድረግ ፍላጎታችን ነበር።

፰ እናም አሁን እነሆ፤ በቅርቡ ፍላጎታ
ችንን እንደፈጸምን አሳይሀለሁ፤ አዎን፣
በጠንካራው ኃይላችን፣ ወይም ከጠንካራ
ኃይላችን ክፍል ጋር፣ የስንቅ አቅርቦትን
ከመቀበላቸው ጥቂት ቀደም ብሎ በምሽት
የቁሜኒን ከተማ ከበብናት።

፱ እናም እንዲህ ሆነ በከተማዋ ዙሪያ
ለበርካታ ምሽት መሸግን፤ ነገር ግን ከነጎ
ራዴያችን ተኝተን ነበር፤ እናም ላማናው
ያን ብዙ ጊዜ እንደሞከሩት በምሽት መጥ
ተው እንዳይገድሉን ጠባቂዎችን አስቀመ
ጥን፤ ነገር ግን ይህን በሚሞክሩበት ጊዜ
ሁሉ ደሞቻቸው ፈሰሶ ነበር።

፲ ከጊዜ በኋላ ስንቆቻቸው ደረሱ፣ እናም
ወደከተማዋ በምሽት ለመግባት ተቃርበው
ነበር። እናም ላማናውያንን ሳይሆን ያገኙት
እኛን ኔፋውያንን ነበር፤ ስለዚህ፣ እነርሱ
ንና ቁሳቁሶቻቸውን ወሰድን።

፲፩ እናም በዚህ ሁኔታ ላማናውያን ከሚ
ደገፉበት ቢቆረጡም፣ እነርሱ ከተማዋን
ለማስቀረት ቆርጠው ነበር፤ ስለዚህ እነ
ዚህን ስንቆች ወስደን ወደ ይሁዳ፣ እናም
እስረኞቻችን በዛራሔምላ መላካችን አስ
ፈላጊ ነበር።

፲፪ እናም እንዲህ ሆነ ብዙ ቀናት ከማለ
ፋቸው በፊት ላማናውያን የእርዳታ ተስፋ

ቸውን ሁሉ ማጣት ጀመሩ፤ ስለዚህ ከተ
ማዋን በእጃችን ሰጡን፤ እናም የቁሜኒን
ከተማ ለማግኘት ያቀድነውን አከናወንን።

፲፫ ነገር ግን እንዲህ ሆነ እስረኞቻችን ብዙ
ስለነበሩ፣ ቁጥራቸው ብዙ ቢሆንም ሠራ
ዊታችንን ሁሉ እስረኞቹን በመጠበቅ እን
ድንጠቀም ወይንም እነርሱን እንድንገድላ
ቸው ተገድደን ነበር።

፲፬ እነሆ በርካታ እስረኞች ያመልጡና
በድንጋይና፣ በዱላ፣ እናም በእጃቸው
ባሉት ማንኛውም ዓይነት መሳሪያዎች ስለ
ሚዋጉን፣ የጦር ምርኮኞች እንዲሆኑ እራሳ
ቸውን አሳልፈው ከሰጡ በኋላ ከሁለት ሺህ
የሚበልጡትን ገድለናል።

፲፭ ስለዚህ ህይወታቸውን ማጥፋት ወይ
ንም እስከ ዛራሔምላ ምድር ድረስም በእ
ጃችን ባለው ጎራዴ መጠበቃችን አስፈላጊ
ሆነብን፤ እናም ደግሞ ከላማናውያን የወ
ሰድናቸው ቢኖረንም፣ ቀለባችን ለራሳች
ንም ሰዎች እንኳን የሚሆን በቂ አልነበረም።

፲፮ እናም አሁን፣ በዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ፣
የጦር ምርኮኞቹን በተመለከተ መወሰን
እጅግ አስቸጋሪ ጉዳይ ነበር፤ ይሁን እንጂ፣
እነርሱን ወደ ዛራሔምላ ምድር ለመላክ
ወሰንን፤ ስለዚህ ሰዎችን መረጥን፣ እናም
ለእስረኞቻችን ወደ ዛራሔምላ ምድር እን
ዲወስዱ ኃላፊነት ሰጠናቸው።

፲፯ ነገር ግን እንዲህ ሆነ በማግስቱ ተመ
ለሱ። እናም አሁን እነሆ፣ እስረኞቹን በተ
መለከተ አልጠየቅናቸውም፤ እነሆም፣
ላማናውያን በእኛ ላይ ነበሩ፣ እናም በጊ
ዜው በእጃቸው ከመውደቅ አድነውን ነበር።
እነሆም፣ አሞሮን እነርሱን ለመርዳት አዲስ
ቀለብና፣ ደግሞ ብዙ ቁጥር ያላቸው ወታ
ደሮችን ልኮላቸው ነበርና።

፲፰ እናም እንዲህ ሆነ ከእስረኞች ጋር የላ
ክናቸው ሰዎች እኛን ለማሸነፍ በተቃረቡ
ጊዜ ላማናውያንን ለመያዝ በወቅቱ ደረሱ።

፲፱ ነገር ግን እነሆ፣ ሁለት ሺህ ስልሳ የሆ
ኑት ወታደሮቼ በኃይል ተዋጉ፤ አዎን፣
በላማናውያን ፊት የማይበገሩም ነበሩ፤
እናም ተቃዋሚዎቻቸውን በሙሉ ገደሉ
አቸው።

፳ እናም ቀሪዎቹ ወታደሮቻችን ከላማና
ውያን ፊት ለመሸሽ በተቃረቡበት ጊዜ፣
እነሆ፣ ሁለት ሺህ ስልሳዎቹ የማይበገሩ
እንዲሁም ተስፋ የማይቆርጡ ነበሩ።

፳፩ አዎን፣ እናም የታዘዙትን ቃላት
በሙሉ በትክክል አከናወኑ፣ እንዲሁም
ጥረት አደረጉ፤ አዎን፣ እንደ እምነታቸ
ውም ለእነርሱ ሆነ፤ እናም [a]ከእናቶቻቸው
የተማሩትን ለእኔ የተናገሩትን ቃላት አስ
ታወስኩኝ።

፳፪ እናም አሁን እነሆ፣ ይህንን ታላቅ
ድል ለማግኘት ያስቻሉ እነዚህ ልጆቼ፣
እናም እስረኞቹን እንዲያጓጉዙ የተመረ
ጡት ሰዎች ነበሩ፤ ላማናውያንን ያሸነፉት
እነርሱ ነበሩና፤ ስለዚህ ወደ ማንቲ ከተማ
ተነድተው ተመለሱ።

፳፫ እናም የቁሜኒ ከተማችንን በመያዝ
ቀጥልን፣ እናም ሁላችንም በጎራዴ አል
ጠፋንም ነበር፤ ይሁን እንጂ ብዙም ጥፋት
ደርሶብናል።

፳፬ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን ከሸሹ
በኋላ፣ ከሞቱት ሰዎቹ መካከል የቀሩት
ቁስለኞች እንዲወሰዱና፣ ቁስላቸው እን
ዲታሰር ትዕዛዝ በፍጥነት ሰጠሁኝ።

፳፭ እናም እንዲህ ሆነ ብዙ ደም ስለፈሰሰ
ባቸው ከእኔ ሁለት ሺዎቹ መካከል ሁለት
መቶ የሚሆኑት እራሳቸውን ስተው ነበር፤
ይሁን እንጂ፣ በእግዚአብሔር ቸርነት፣
እናም ለመደነቃችንና፣ ደግሞ ለሠራዊታ
ችን ደስታ መሰረት፣ ከእነርሱ [b]አንድም
ነፍስ አልጠፋብንም ነበር፤ አዎን፣ እናም
ከእነርሱ መካከልም በብዙ ያልቆሰለ አን
ድም ነፍስ አልነበረም።

፳፮ እናም አሁን፣ መጠበቃቸው ለሠ
ራዊታችን ሁሉ አስገራሚ ነበር፤ አዎን፣
በሺዎች የሚቆጠሩት ወንድሞቻችን በተገ
ደሉ ጊዜ እነርሱ ተርፈው ነበር። እናም ይህ
የሆነው ፃድቅ እግዚአብሔርም እንዳለና፣
ማንም ካልተጠራጠረ [c]በእግዚአብሔር

፳፩ a አልማ ፱፯፡ ፳፯–፳፰። ፳፭ b አልማ ፱፯፡ ፱፯። ፳፮ c ቅ.መ.መ. ሀይል።

አስደናቂው ኃይል እንደሚጠበቅ ᵃእንዲ ያምኑ በተማሩት ባላቸው ታላቅ እምነት የተነሳ በኃያሉ እግዚአብሔር ድንቅ ስራ እንደሆነ በትክክል እናመለክታለን።

፳፯ እንግዲህ እነዚህ የተናገርኩባ ቸው እምነት ይህ ነበር፤ እነርሱ ወጣቶች ናቸው፣ እናም አስተሳሰባቸው ፅኑ ነው፣ እናም እምነታቸውን ሳያቋርጡ በእግዚአ ብሔር አድርገዋል።

፳፰ እናም እንግዲህ እንዲህ ሆነ የቆሰ ሉትን ሰዎች ከተንከባከብንና፣ የሞቱብ ንን፣ እናም ደግሞ ብዙ የነበሩትን የሞቱ ትን ላማናውያን ከቀበርን በኋላ፣ እነሆ፣ ወደ ዛራሔምላ ምድር ይዘዋቸው ጉዞ ስለ ጀመሩት እስረኞች በተመለከተ ጊድን ጠየ ቅነው።

፳፱ እንግዲህ ጊድ ምድሪቱ እየጠበቁ እን ዲወስዷቸው በተመደቡት ቡድኖች ላይ የተሾመው ሊቀ ሽምበላቸው ነበር።

፴ እናም አሁን፣ ጊድ የተናገረኝ ቃላት እነዚህ ናቸው፤ እነሆ፣ ከእስረኞቻችን ጋር ወደ ዛራሔምላ ምድር ጉዞ ጀምረን ነበር። እናም እንዲህ ሆነ የላማናውያንን የጦር ሰፈር እንዲጠብቁ የተላኩትን የሠራዊታ ችንን ሰላዮች አገኘናቸው።

፴፩ እናም እንዲህ ሲሉ ወደ እኛ ጮኹ— እነሆ፣ የላማናውያን ሠራዊት ወደ ቁሜኒ ከተማ በመሄድ ላይ ናቸው፣ እናም እነሆ፣ ላማናውያን ያጠቋቸዋል፤ አዎን፣ እናም ህዝባችንን ያጠፋሉ።

፴፪ እናም እንዲህ ሆነ እስረኞቻችን እንዲበረቱ ያደረጋቸውን ጩኸታቸውን ሰሙ፤ እናም በአመፅ በእኛ ላይ ተነሱ።

፴፫ እናም እንዲህ ሆነ በማመፃቸው ጎራዴዎቻችንን በእነርሱ ላይ አሳረፍንባ ቸው። እናም እንዲህ ሆነ በአንድነትም ወደ ጎራዴው ሮጡ፣ በእርሱም ብዙ ቁጥር ያላ ቸው ተገደሉ፤ እናም ቀሪዎቹ አመለጡና፣ ከእኛ ሸሹ።

፴፬ እናም እነሆ፣ በሸሹ ጊዜ፣ እኛም ልንደርስባቸውም ስላልቻልን፣ ጉዞአች ንን በፍጥነት ወደ ቁሜኒ ከተማ አደረግን፤ እናም እነሆ፣ ወንድሞቻችን ከተማዋን እን ዲጠብቁ እንረዳቸው ዘንድ በጊዜ ደረስን።

፴፭ እናም እነሆ ከጠላቶቻችን እጅ በድ ጋሚ አመለጥን። እናም የአምላካችን ስም የተባረከ ይሁን፤ እነሆም እርሱ ነው እን ድንተርፍ ያደረገን፤ አዎን፣ ይህንን ታላቅ ነገር ለእኛ አድርጎልናል።

፴፮ እንግዲህ እንዲህ ሆነ የጊድን ቃል፣ እኔ ሔለማን፣ በሰማሁኝ ጊዜ፣ እኛን እን ዳንጠፋ በመጠበቅ በነበረው በጌታ ቸር ነት በታላቅ ደስታ ተሞልቼ ነበር፤ አዎን፣ እናም የሞቱት ነፍስም በአምላካቸው ዘንድ ᵇእንደሚያርፍ አምናለሁ።

ምዕራፍ ፶፰

ሔለማን፣ ጊድ፣ እና ቴአምነር የማን ቲን ከተማ በዘዴ ወሰዱ—ላማናውያን ወጡ—የአሞን ህዝቦች ወንድ ልጆች ነፃነታቸውን፣ እና እምነታቸውን ለመ ከላከል ፀንተው በቆሙ ጊዜ ተጠበቁ። ከ፳፫–፳፪ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እነሆ፣ እንዲህ ሆነ የሚቀጥለው ዓላማችን የማንቲን ከተማ መያዝ ነበር፤ ነገር ግን እነሆ፣ በጥቂት ሰዎቻችን ከከተ ማቸው ለማስወጣት አይቻለንም ነበር። እነ ሆም፣ ቀደም ሲል ያደረግነውን ያስታውሱ ነበር፤ ስለዚህ ከጠንካራ ምሽጋቸው ᶜበዘዴ ለማስወጣት አልተቻለም ነበር።

፪ እናም በቁጥርም ከእኛ ወታደሮች የሚ ልቁ ስለነበር ወደ ጠንካራው ምሽጋቸው በመሄድ ለማጥቃት አልደፈርንም ነበር።

፫ አዎን፣ እናም እኛ መልሰን የወሰድናቸ ውን እነዚያን የምድሮች ክፍል ለመጠበቅ ሰዎቻችንን መጠቀም አስፈላጊ ነበር፤ ስለ ዚህ ከዛራሔምላ ምድር ወታደራዊ ኃይል፣ እናም ደግሞ አዳዲስ ስንቆችን እናገኝ ዘንድ መጠበቁ አስፈላጊ ነበር።

፬ እናም እንዲህ ሆነ ስለህዝባችን ጉዳይ እንዲያውቅ ለማድረግ ወደ ምድራችን ገዢ

መልዕክተኛ ላክሁኝ። እናም እንዲህ ሆነ ከዛራሔምላ ምድር ስንቆችንና፣ ወታደራዊ ኃይልን ለማግኘት ጠበቅን።

፮ ነገር ግን እነሆ፣ ይህ ጥቂቱ ብቻ ነበር የጠቀመን፤ ምክንያቱም ላማናውያንም ደግሞ ከቀን ወደ ቀን ታላቅ ብርታትን ይቀበላሉ ነበርና፤ እናም ደግሞ በርካታ ስንቆችን፤ እናም በዚህ ጊዜ የነበርንበት ሁኔታዎች እነኚህ ነበሩ።

፯ እናም ላማናውያን ከጊዜ ወደጊዜ እኛን ለማጥቃት ገሰገሱ፣ እናም እኛን ለማጥፋትም ስልት ቀየሱ፤ ይሁን እንጂ በማፈግፈጋቸውና በጠንካራው ምሽጋቸው ምክንያት ከእነርሱ ጋር ለመዋጋት ለመምጣት አልቻልንም።

፰ እናም እንዲህ ሆነ ምግብ አጥተን ልንጠፋ እስከምንቃረብ ድረስ በእንደዚህ ዓይነት አስቸጋሪ ሁኔታ ለብዙ ወራት ጠበቅን።

፱ ነገር ግን እንዲህ ሆነ እኛን ለመርዳት ሲባል በሁለት ሺህ ሠራዊት የተጠበቀ ምግብ ተቀበልን፤ እናም እራሳችንንና ሀገራችንን በጠላት እጅ እንዳይወድቁ አዎን ስፍር ቁጥር ከሌላቸው ጠላቶች ጋር ለመዋጋት የተቀበልነው እርዳታ ሁሉ ይህ ነው።

፱ እናም እንግዲህ ይህ ለችግሩ መንስኤ ምን እንደሆነ፣ ወይም ተጨማሪ ኃይል ለምን እንዳልላኩልን ምክንያቱን አናውቅም፤ ስለዚህ አዝነን ነበር፣ እናም ደግሞ በማንኛውም መንገድ የእግዚአብሔር ፍርድ በምድራችን ላይ ይሆናል፣ ውጤቱም ለእኛ መሸነፍ፣ እናም ፍፁም ጥፋት ይሆናል በሚል ፍርሃት ተሞልተን ነበር።

፲ ስለዚህ እግዚአብሔር እንዲያበረታንና፣ ከጠላቶቻችን እጅ እንዲያድነን፣ አዎን፣ እናም ደግሞ ህዝባችንን ለመርዳት፣ ከተሞቻችንንና፣ ምድራችንን፣ እናም ሀብታችንን እናስመልስ ዘንድ ብርታትን ይሰጠን ዘንድ ከልባችን ፀለይን።

፲፩ አዎን፣ እናም እንዲህ ሆነ ጌታ አምላካችን እኛን እንደሚያድነን ለማረጋገጥ ጎብኝቶናል፤ አዎን፣ ለነፍሳችን ሰላምን ተናግሮናል፣ ታላቅ እምነትንም ሰጥቶናል፣ እናም በእርሱም ለመዳናችን ተስፋ እንዲኖረን አድርጓል።

፲፪ እናም ጠላታችንን ለማሸነፍና፣ ምድራችንንና፣ ሀብታችንንና፣ ሚስቶቻችንንና፣ ልጆቻችንንና፣ [ሀ]የነፃነታችን መንስኤ የሆኑትን [ለ]መጠበቅ ወሰንን፣ ባገኘነውም ጥቂት ኃይል ድፍረትን አገኘን።

፲፫ እናም ባለን ኃይል ሁሉ በማንቲ ከተማ ወደነበሩት ላማናውያን ሄድን፤ እናም በከተማዋ አቅራቢያ በሚገኘው ምድረበዳ ድንኳኖቻችንን ተከልን።

፲፬ እናም እንዲህ ሆነ በሚቀጥለው ቀን፣ በከተማዋ አጠገብ በምድረበዳው ዳርቻ መሆናችንን ላማናውያን በተመለከቱ ጊዜ፣ የወታደሮቻችንን ቁጥር እንዲሁም ጥንካሬ ለማወቅ ሰላዮቻቸውን ላኩብን።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ እንደቁጥራችን ብዛት ጠንካራ አለመሆናችንን በተመለከቱ ጊዜ፣ እናም ከእኛም ጋር ለመዋጋትና፣ እኛን ለመግደል የማይመጡ ከሆነ፣ እርዳታው ይቋረጥብናል ብለው በመፍራትና ደግሞ በበርካታ ሰራዊታቸው በቀላሉ ልናጠፋቸው እንችላለን ብለው በመገመታቸው፤ ስለዚህ ከእኛ ጋር ለመዋጋት ዝግጅት ጀመሩ።

፲፮ እናም ከእኛ ጋር ለመዋጋት ዝግጅት ማድረጋቸውን በተመለከትን ጊዜ፣ እነሆ፣ ጊድ ከጥቂት ሰዎቹ ጋር እራሱን በምድረበዳው እንዲሸሽግ አደረግሁ፣ ደግሞም ቲኦመነርና ጥቂት ሰዎች እራሳቸውን በምድረበዳው እንዲሸሽጉ አደረግሁ።

፲፯ እንግዲህ ጊድና የእርሱ ሰዎች በስተቀኝ በኩል፣ እናም የተቀሩት በስተግራ በኩል ነበሩ፤ እናም እራሳቸውን በሸሸጉ ጊዜ፣ እነሆ፣ ላማናውያን ከእኛ ጋር ለመዋጋት በመጀመሪያ ጊዜ በወጡበት ድንኳናችንን በተከልንበት ስፍራ፣ ከተቀሩት ወታደሮቼ ጋር ቀረሁ።

፲፰ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን ከበርካታ ሠራዊቶቻቸው ጋር በእኛ ላይ መጡ።

ፊ ሀ ቅ.መ.መ. መብት። ለ አልማ ፶፯፡ ፲፪–፲፫፣ ሞር. ፪፡ ፳፫።

እናም በመጡ ጊዜና በጎራዴ ሊያጠቁን በተቃረቡ ጊዜ፤ ከእኔ ጋር የነበሩትን ህዝቦቼን ወደ ምድረበዳው እንዲያፈገፍጉ አደረግሁ።

፲፱ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን እኛን ይገድሉን ዘንድ በጣም እጅግ ፍላጎታቸው በታላቅ ፍጥነት ተከተሉን፤ ስለዚህ ወደ ምድረበዳው ተከተሉን፤ በጊድ፣ እናም በቲአምነር መካከል ስናልፍም በላማናውያን አልተገኙም ነበር።

፳ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን ባለፉ ጊዜ፣ ወይንም ሠራዊቱ ባለፉ ጊዜ፣ ጊድና ቴኦምነር ከተሸሸጉበት ስፍራ ወጡ፤ እናም ወደከተማዋ እንዳይመለሱ የላማናውያን ሰላዮችን ቆርጠው አስቀሩአቸው።

፳፩ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን ቆርጠው ካስቀሩአቸው በኋላ፣ ወደ ከተማዋ ሮጡና እስከሚያጠፉአቸው፣ እናም ከተማዋንም እስከሚወስዱ ድረስ፣ ከተማዋን እንዲጠብቁ የቀሩትን ጠባቂዎች አጠቁ አቸው።

፳፪ እንግዲህ ይህ የሆነው ከጥቂት ጠባቂዎቻቸው በስተቀር ወደ ምድረበዳው እንዲሄዱ ላማናውያን ለሠራዊቶቻቸው በሙሉ ስለፈቀዱላቸው ነበር።

፳፫ እናም እንዲህ ሆነ ጊድና ቴኦምነር በዚህ ዘዴ ጠንካራ ምሽጋቸውን ወሰዱ። እናም እንዲህ ሆነ ወደ ዛራሔምላ በምድረበዳው ብዙ ከተጓዝን በኋላ፣ ወደ አንድ አቅጣጫ ተጓዝን።

፳፬ እናም ላማናውያን ወደ ዛራሔምላ ምድር መዝመታቸውን በተመለከቱ ጊዜ፣ እጅግ ፈሩ፣ ይህም የሆነበት ወደ ጥፋት የሚመራቸው ዕቅድ የተዘጋጀ መስሏቸው ስለነበር ነው፤ ስለዚህ በድጋሚ ወደ ምድረበዳው ማፈግፈግ ጀመሩ፤ አዎን፣ በመጡበት መንገድም ተመለሱ።

፳፭ እናም እነሆ፣ ምሽት ነበርና፣ ድንኳናቸውን ተክለው ነበር፣ ምክንያቱም የላማናውያን ዋና አዛዦች ኔፋውያን በጉዞ አቸው ደክመዋል በማለት ገምተው ነበር፤ እናም ወታደሮቻቸውን ሁሉ ከፊት እንዳስወጡ ስለገመቱ፣ በዚህም የተነሳ የማንቲን ከተማ በተመለከተ አላሰቡባትም ነበር።

፳፮ እንግዲህ እንዲህ ሆነ ምሽት በሆነ ጊዜ፣ የእኔ ሰዎች እንዳይተኙ፣ ነገር ግን በሌላ አቅጣጫ ወደ ማንቲ ምድር ወደፊት እንዲሄዱ አደረግሁ።

፳፯ እናም በዚህ በምሽቱ ጉዞአችን የተነሳ፤ እነሆ፣ በሚቀጥለው ቀን ላማናውያን በርቀት ቀድመናቸው ስለነበር አስቀድመን ወደ ማንቲ ከተማ ደረስን።

፳፰ እናም እንዲህ ሆነ በዚህ ዓይነት ስልት፣ ደም መፋሰስ ሳይኖር፣ የማንቲን ከተማ ያዝን።

፳፱ እናም እንዲህ ሆነ የላማናውያን ወታደሮች በከተማዋ አጠገብ በደረሱ ጊዜና፣ ከእነርሱ ጋር ለመገናኘት መዘጋጀታችንን በተመለከቱ ጊዜ፣ እጅግ ተገርመው ነበር፣ እናም ወደ ምድረበዳው እስከሚሸሹ ድረስ በታላቅ ፍርሃት ተውጠው ነበር።

፴ አዎን፣ እናም እንዲህ ሆነ የላማናውያን ሠራዊት ከምድሪቱ ክፍል ሁሉ ሸሽተው ነበር። ነገር ግን እነሆ፣ ብዙ ሴቶችንና ልጆችን ይዘው ከምድሪቱ ወጡ።

፴፩ እናም በላማናውያን የተወሰዱት ᵐእነዚያ ከተሞች ሁሉ በዚህን ጊዜ በእኛ ቁጥጥር ሥር ናቸው፤ እናም በላማናውያን ምርኮኞች ሆነው ከተወሰዱት በቀር አባቶቻችንና፣ ሴቶቻችን፣ እናም ልጆቻችን ወደ ቤታቸው ተመለሱ።

፴፪ ነገር ግን እነሆ፣ ወታደሮቻችን በቁጥር በርካታ የሆኑትን ከተሞች፣ እና በርካታ ንብረቶች ለመጠበቅ ጥቂት ናቸው።

፴፫ ነገር ግን እነሆ፣ የእኛ የነበሩትን ስፍራዎች፣ እናም ከተሞች እስከምናገኝ ድረስ በምድሪቱ ላይ ድልን በሰጠን አምላካችን እምነት አለን።

፴፬ እንግዲህ መንግስት የበለጠ ድጋፍን ለእኛ የማይሰጥበትን መንስኤ እናውቅም፤ ወደ እኛ የመጡትም ሰዎች ለምን ታላቅ ድጋፍ እንዳላገኘን አያውቁም።

፴፭ እነሆ፣ ድል እንዳላገኛችሁ ለመሆን እንደሚችል፣ እናም ወታደሮችን ወደዚያ ምድር ወስደህም እንደሆነ እንገምታለን፤ ይህ ከሆነ ለማጉረምረም አንፈልግም።

፴፮ እናም ይህ ካልሆነ፣ እነሆ፣ ስለዚህ በመንግስት [ሀ]መከፋፈል ምክንያት በተጨማሪ ሰዎችን ለእኛ እርዳታ እንደማይልኩ እንፈራለን፣ ከላኳቸው የበለጠ በቁጥር ብዙ መሆናቸውን እናውቃለንና።

፴፯ ነገር ግን እነሆ ይህ ምንም ማለት አይ ደለም—ምንም እንኳን ወታደሮቻችን ደካሞች ቢሆኑ፣ እግዚአብሔር [ለ]እንደሚያድነን እናምናለን፤ አዎን፣ እናም ከጠላቶቻችን እጅ ያስለቅቀናል።

፴፰ እነሆ፣ ይህ በሀያ ዘጠነኛው ዓመት መጨረሻ ነበር፣ እኛም ምድሮቻችንን ይዘናል፤ እናም ላማናውያን ወደ ኔፊ ምድር ሸሽተዋል።

፴፱ እናም በከፍተኛ ሁኔታ የተናገርኳቸው የአሞን ህዝቦች ወንድ ልጆች፣ በማንቲ ከተማ ከእኔ ጋር ናቸው፤ ጌታም ረድቷቸዋል፣ አዎን፣ እናም [ሐ]አንድም ነፍስ እንኳን እስከማይጠፋ ድረስ በጎራዴ እንዳይጠፉ ተጠብቀዋል።

፴ ነገር ግን እነሆ፣ በብዛት ቆስለዋል፣ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ነፃ ባደረጋቸው በዚያ [መ]ነፃነት በፅኑነት ቆመዋል፤ እናም ከቀን ወደ ቀንም ጌታ አምላካቸውን በማስታወስ ጠንቃቆች ናቸው፤ አዎን፣ ህጎቹንና፣ ፍርዱን፣ እንዲሁም ትዕዛዛቱን፣ ለመጠበቅ ጥረት አድርገዋል፤ እናም የሚመጣውን በተመለከተ ስለተተነበየው እምነታቸውም ጠንካራ ነው።

፴፩ እናም አሁን፣ የተወደድህ ወንድሜ ሞሮኒ፣ እኛን የፈወሰንና፣ ነፃ ያደረገን ጌታ አምላካችን፣ ያለማቋረጥ በፊቱ ይጠብቅህ፤ አዎን፣ እናም ህዝቦቹን ይውደድ፣ ለእኛም እርዳታ የነበሩትን ላማናውያን የወሰዱብንን ንብረቶች ለማግኘት ድል እንድታገኝ እርሱ ይርዳህ። እናም እንግዲህ፣ እነሆ ደብዳቤዬን እደመድማለሁ። እኔ ሔለማን፣ የአልማ ልጅ ነኝ።

ምዕራፍ ፶፪

ሞሮኒ የሔለማንን ወታደሮችን እንዲያጠናክር ፓሆራንን ጠየቀው—ላማናውያን የኔፋውያን ከተማ ያዙ—ሞሮኒ በመንግስቱ ላይ ተናደደ። በ፷፪ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እንግዲህ እንዲህ ሆነ በኔፊ ህዝብ ላይ በመሣፍንቱ ሠላሳኛ ዓመት የንግስ ዘመን ሞሮኒ የሔለማንን [ሀ]ደብዳቤ ተቀብሎ ካነበበ በኋላ፣ በደህንነቱ አዎን፣ ሔለማን የተቀሙትን ምድሮች ለማግኘት ባደረገው ታላቅ ድል እጅግ ተደሰቶ ነበር።

፪ አዎን እናም ሞሮኒ እርሱ በነበረበትም ምድር ሁሉ ዙሪያ ያሉት ይደሰቱ ዘንድ ለህዝቡ ይህ ሁሉ እንዲታወቅ አስደረገ።

፫ እናም እንዲህ ሆነ ሞሮኒ በአስደናቂ ሁኔታ በድጋሚ ያገኟቸውን ምድሮች ለመጠበቅ እንዲችሉ፣ ሔለማንን ወይንም የሔለማን ወታደሮችን ለማበርታት ሰዎች እንዲሰባሰቡ እንደፈለገ [ለ]ለፓሆራን በፍጥነት [ሐ]ደብዳቤ ላከ።

፬ እናም እንዲህ ሆነ ሞሮኒ ወደ ዛራሔምላ ምድር ይህንን ደብዳቤ በላከ ጊዜ፣ የቀሩትንና ላማናውያን የወሰዱባቸውን ከተሞች ያገኝ ዘንድ በድጋሚ ዕቅድ ማቀድ ጀመረ።

፭ እናም እንዲህ ሆነ ሞሮኒ ከላማናውያን ጋር ለመዋጋት ዝግጅት በሚያደርግበት ጊዜ፣ እነሆ፣ ከሞሮኒ ከተማና፣ ከሌሂ ከተማና፣ ከሞሪያንተን ከተማ የተሰባሰቡት የኔፋውያን ሰዎች በላማናውያን ጥቃት ደረሰባቸው።

፮ አዎን፣ ከማንቲ ምድር እናም በዙሪያው ካለው ምድር እንዲሸሹ የተገደዱትም በዚህች ምድር ከላማናውያን ጋር ሊቀላቀሉ መጡ።

፴፮ *ሀ* አልማ ፳፭፡ ፩–፭።
፴፯ *ሀ* ፪ ነገሥ. ፲፯፡ ፴፭–፴፱።
፴፱ *ሀ* አልማ ፶፮፡ ፶፯።

፴ *ሀ* ቅ.መ.መ. መብት።
፶፱ *ሀ* አልማ ፶፮፡ ፩።
ለ አልማ ፳፡ ፩–፫።
፫ *ሀ* አልማ ፶፡ ፴።
፬ *ሀ* ፲ ነገሥ. ፲፡ ፴–፴፭።
፭ *ሀ* ፲ ነገሥ. ፲፡ ፴–፴፭።
፮ *ሀ* ፲ ነገሥ. ፲፡ ፴–፴፭።

፲ እናም በቁጥር እጅግ ብዙ ስለነበሩ፣ አዎን፣ እናም በአሞሮን ትዕዛዝ ከቀን ቀን ጥንካሬን በማግኘታቸው በኔፋውያን ሰዎች ላይ መጡና፣ በአሰቃቂ ሁኔታ ያጠቁአቸ ውና ይገድሉአቸው ጀመሩ።

፲፩ እናም ወታደሮቻቸው በቁጥር ብዙ ስለነበሩ የተቀሩት የኒፋያህ ሰዎች እንዲ ሸሹ ተገደዱ፤ እናም ከሞሮኒ ሠራዊት ጋር ተቀላቀሉ።

፲፪ እናም እንግዲህ ከተማዋን ህዝቡ እን ዲጠብቅ ለመርዳት ሞሮኒ ወደ ኔፋውያን ከተማ ሰዎች ተልከዋል ብሎ ገምቶ ነበር፣ እናም ከተማዋን ከእነርሱ እጅ ዳግም ከመ ውሰድ ይልቅ በላማናውያን እጅ እንዳይገባ መጠበቁ ቀላል መሆኑን በማወቁ ከተማ ዋን በቀላሉ ይጠብቋታል ብሎ ገምቶ ነበር።

፲፫ ስለዚህ የያዛቸውን ስፍራዎች ለመጠ በቅ ኃይሉን ከእርሱ ጋር አስቀርቶ ነበር።

፲፬ እናም እንግዲህ፣ ሞሮኒ የኔፋውያን ከተማ መወሰዷን በተመለከተ ጊዜ እጅግ አዝኖ ነበር፣ እናም በህዝቡ ክፋት የተነሳ በወንድሞቻቸው እጅ መውደቅ እንደሚ ገባቸው መጠራጠር ጀመረ።

፲፭ እንግዲህ ዋና ሻምበሎች የነበራቸው ጥርጣሬ ይህ ነበር። እነርሱም በህዝቦች ክፋት ምክንያት ተጠራጠሩና ተደነቁ፣ እናም ይህ የሆነው ላማናውያን በእነርሱ ላይ ድል በማግኘታቸው ነው።

፲፮ እናም እንዲህ ሆነ ሞሮኒ የሀገራቸውን ነፃነት በተመለከተ በመንግስቱ "ግዴለሽነት ተቆጥቶ ነበር።

ምዕራፍ ፷

ሞሮኒ መንግስቱ ሠራዊቱን ችላ ማለ ቱን በተመለከተ ለፓሆራን ወቀሳ አቀ ረበ—ጌታ ፃድቃኖች እንዲገደሉ ይፈቅ ዳል—ኔፋውያን ከጠላቶቻቸው እራሳቸ ውን ለማስለቀቅ ያላቸውን ኃይል እንዲ ሁም ዘዴዎች በሙሉ መጠቀም ይኖርባ ቸዋል—ሞሮኒ ለሠራዊቱ እርዳታ ካልተ ደረገ ከመንግስት ጋር እንደሚዋጋ አስጠ ነቀቀ። በ፷፪ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ ሞሮኒ ለሀገሪቱ አስ ተዳዳሪ፣ ለፓሆራን በድጋሚ ፃፈና፣ የፃ ፈውም ቃል እንዲህ ይል ነበር፥ እነሆ፣ በዛራሔምላ ከተማ "ዋና ዳኛና፣ በምድ ሪቱ አስተዳዳሪ ለሆነው ለፓሆራን፣ እናም ደግሞ የጦር ጉዳያቸውን በተመለከተ እን ዲያስተዳድሩና እንዲመሩ ከእነዚህ ሁሉ መካከል በህዝብ ለተመረጡት፣ ደብዳቤዬን አቀርባለሁ።

፪ እነሆም፣ በወቀሳ መልክ ለእነርሱ በመ ጠኑ የምለው አለኝ፤ እነሆም፣ እናንተ ራሳ ችሁም ሰዎችን በአንድ ላይ እንድትሰበስ ቡና፣ በጎራዴና፣ በሻምላ፣ እንዲሁም በሁ ሉም ዓይነት የጦር መሳሪያዎች እንድታስ ታጥቁ እናም ላማናውያን ወደ ምድራችን በመጡበት በየትኛውም አቅጣጫ እንድት ልኩአቸው ተሹማችኋል።

፫ እናም እንግዲህ እነሆ፣ እኔ ራሴና፣ ደግሞ የእኔ ሰዎችና፣ ደግሞ ሔለማን፣ እና የእርሱ ሰዎች ታላቅ የሆነን ስቃይ ተሰቃይ ተናል፤ አዎን፣ በረሃብ፣ በጥማትና፣ በድ ካም፣ እናም በሁሉም ዓይነት ስቃይ ተሰ ቃይተናል።

፬ ነገር ግን እነሆ፣ የተሰቃየነው ይህ ሁሉ ቢሆን ኖሮ፣ አናጉረመርምም እንዲሁም ወቀሳ አናቀርብም ነበር።

፭ ነገር ግን እነሆ፣ በህዝባችን መካከል ግድያው ከፍተኛ ነበር፣ አዎን፣ በሺህ የሚ ቆጠሩ በጎራዴው ወድቀዋል፣ ለወታደሮ ቻችን በቂ ብርታትንና እርዳታን ብታደ ርጉ ኖሮ፣ ውጤቱም ሌላ በሆነ ነበር። አዎን በእኛም ላይ ችላ ባይነታችሁ ታላቅ ነበር።

፮ እናም እንግዲህ እነሆ፣ የዚህ እጅግ ታላቅ የሆነ ችላ ባይነት መንስኤን ማወቅ እንፈልጋለን፤ አዎን፣ ለሀሳብ የለሽነትታ ችሁ ምክንያትን ማወቅ እንፈልጋለን።

፯ ጠላቶቻችሁ በዙሪያችሁ የሞትን ስራ በሚያስራጨበት ወቅት በዙፋናችሁም

ምንም ሳታስቡ ለመቀመጥ እንችላለን ብላ ችሁ ታስባላችሁን? አዎን፣ በሺህ የሚቆ ጠሩ ወንድሞቻችሁን ሲገድሉባችሁ—

፰ አዎን፣ ለእርዳታ ወደእናንተ የሚመ ለከቱትንም፤ አዎን በእናንተም እንዲደገፉ በምትገኙበት ቦታ ያስቀምጡአችሁ ሲገ ድሉባችሁ፣ አዎን፣ ወታደሮችን እንዲ ያበረቱአቸው ወደእነርሱ ለመላክ፣ እናም ብዙ ሺህ የሚሆኑትን በጎራዴ ከመቆረጥ ባዳናችሁ ነበር።

፱ ነገር ግን እነሆ፣ ይህ ብቻም አይደ ለም—ብዙዎች ለዚህ ህዝብ ደህንነት ታላቅ ፍላጎት ስለነበራቸው እስከሚዋጉ፣ እናም ደማቸው ፈሶም እስከሚሞቱ ድረስ ስንቃ ችሁን ያዛችሁባቸው፤ አዎን፣ እናም ለእ ነርሱ እጅግ ታላቅ የሆነ ግዴለሽነት ስለነ በራችሁ ይህንን ያደረጉት በረሃብ ″ሊጠፉ ሲቃረቡ ነበር።

፲ እናም እንግዲህ፣ የተወደዳችሁ ወን ድሞቼ—የምትወደዱ መሆን ነበረባችሁ፤ አዎን፣ እናም ለዚህ ህዝብ ደህንነትና፣ ነፃ ነት ይበልጥ በትጋት ራሳችሁን ማነሳሳት ነበረባችሁ፤ ነገር ግን እነሆ በሺህ የሚቆጠ ሩት ሰዎች ደም ለበቀል በራሳችሁ ላይ እስ ከሚመጣ ድረስ ችላ አላችኋቸው፤ አዎን፣ ጩኸታቸው፣ እናም ስቃያቸው ሁሉ በእ ግዚአብሔር ዘንድ የታወቀ ነው—

፲፩ እነሆ፣ እናም በታላቁ የእግዚአብሔር ቸርነት ምክንያት ምንም ነገር ሳትፈፅሙ ያድነናል፣ እርሱም ትቶአችሁ በዙፋናችሁ ላይ መቀመጥ እንችላለን ብላችሁ ትገምታ ላችሁን? እነሆ፣ ይህንን የምትገምቱ ከሆነ ግምታችሁ ከንቱ ነው።

፲፪ ብዙዎች ወንድሞቻችሁ ስለሞቱ በኃ ጢአታቸው ነው የተገደሉት ብላችሁ ″ትገ ምታላችሁን? እኔ እላችኋለሁ፣ እንደዚህ የምትገምቱ ከሆነ ግምታችሁ ከንቱ ነው፤ እንዲህ እላችኋለሁና፣ ብዙዎች በጎራዴ ሞተዋል፤ እናም እነሆ ይህ ኩነኔያችሁ ነው፤

፲፫ ጌታ ትክክለኛው ፍርዱና ቅጣቱ በኃ ጢአተኞች ላይ ይሆን ዘንድ ″ፃድቃኖች እንዲገደሉ ይፈቅዳል፤ ስለዚህ ፃድቃኖች ስለተገደሉ የጠፉ ናቸው ብላችሁ አትገ ምቱ፤ ነገር ግን እነሆ በጌታ በአምላካቸው ዘንድ ያርፋሉ።

፲፬ እናም አሁን እነሆ፣ እላችኋለሁ እጅግ ሰነፎች በመሆናቸው፤ አዎን፣ በመንግስ ታችንም ስንፍና ቢሆን፣ እናም ለወንድ ሞቻቸውም፣ አዎን፣ ለተገደሉትም ቢሆን ባላቸው ታላቅ ችላ ባይነት፣ የእግዚአብ ሔር ቅጣት በእነዚህ ሰዎች ላይ እንዳይሆን በጣም እፈራለሁ።

፲፭ በአመራራችን በተጀመረው ″ኃጢያት ባይሆን ኖሮ ጠላቶቻችን በእኛ ላይ ኃይልን እንዳያገኙ ለመቋቋም ይቻለን ነበር።

፲፮ አዎን፣ በራሳችን መካከል በተጀመ ረው ″ጦርነት ባይሆን ኖሮ፤ አዎን፣ በራ ሳችን መካከል ብዙ ደም መፋሰስ እንዲ ሆን ባደረጉት በንጉሡ ሰዎች ባይሆን ኖሮ፤ አዎን፣ በመካከላችን ፀብ በነበረበት ጊዜ፣ ቀደም ሲል እንዳደረግነው እራሳችንን በአ ንድ ላይ ብናደርግ ኖሮ፤ አዎን፣ ″የንጉስ ሰዎች በእኛ ላይ እንደፈለጉት ኃይልና ስል ጣን ባይሆን ኖሮ፤ በመካከላችን ለብዙ ደም መፋሰስ ምክንያት የሆነውን ጎራዴአቸውን ከማንሳት ይልቅ፣ ለነፃነታችን ምክንያት እውነተኞች ቢሆኑ፣ እናም ከእኛ ጋር ተቀ ላቅለው በጠላቶቻችን ላይ ቢሄዱ፣ አዎን፣ በጌታ ብርታት ወደ እነርሱ ብንሄድ ጠላ ቶቻችንን እንበታትናቸው ነበር፣ ምክን ያቱም ይህ የሚሆነው የጌታ ቃሉ ይፈፀም ዘንድ ነው።

፲፯ ነገር ግን እነሆ፣ ላማናውያን ምድራ ችንን ለመውሰድ መጥተዋል፣ እናም ህዝ ባችንን በጎራዴ እየገደሉ፤ አዎን፣ ሴቶቻ ችንንና፣ ልጆቻችንን፣ እናም ደግሞ ምር ኮኞች አድርገው እየወሰዱአቸው ናቸው፣ ሁሉንም ዓይነት ስቃይ እንዲሰቃዩ እያደ

፱ ″ አልማ ፱፰፡ ፲።
፲፪ ″ ሉቃ. ፲፫፡ ፩–፭።
፲፫ ″ አልማ ፲፡ ፲–፲፩፤
ት. እና ቃ. ፵፪፡ ፵፯–፵፯።
፲፭ ″ አልማ ፱፩፡ ፱፣ ፲፫።
፲፮ ″ አልማ ፱፩፡ ፲፯–፲፱።
ለ አልማ ፱፩፡ ፭፣ ፰።

ረጉአቸው ናቸው፤ ይህም ኃይልና ሥል ጣን በሚሹ ታላቅ ኃጢያት፣ አዎን፣ እንዲ ሁም በእነዚያ የንጉስ ሰዎች ምክንያት ነው።

፲፰ ነገር ግን ይህንን በተመለከተ ለምን ብዙ እላለሁኝ? እራሳችሁም ብትሆኑ ስል ጣንን የምትፈልጉ መሆናችሁን አናው ቅም። እናንተ ለሀገራችሁ ከሀዲ እንደሆ ናችሁም አናውቅም።

፲፱ ወይም ችላ ያላችሁን፣ ምግብም እን ዳይላክልን እናም ደግሞ ወታደሮቻችን እንዲጠናከሩ ሰዎች እንዳይላኩ ያደረጋ ችሁበት ምክንያት በሀገራችን ዋና ስፍራ በመሆናችሁ፣ እናም በጠባቂዎች በመከ በባችሁ ነውን?

፳ የጌታ የአምላካችሁን ትዕዛዛት ረስታች ኋልን? አዎን አባቶቻችን በምርኮ እንደነበ ሩስ ረስታችኋልን? ከጠላቶቻችን እጅ ብዙ ጊዜ መለቀቃችንን ረሳችሁትን?

፳፩ ወይም በዙፋናችን እንደተቀመጥን እና ጌታ የሰጠንን ዘዴዎች ሳንጠቀምባ ቸው ያድነናል ብላችሁ ትገምታላችሁን?

፳፪ አዎን፣ በሺዎች እንዲሁም በአስር ሺዎች ያለስራ በተቀመጡት ተከብባችሁ፤ በዙሪያችሁ በምድሪቱ ዳርቻ በሺህ የሚ ቆጠሩት በጎራዴ በተገደሉ ጊዜ፤ አዎን፣ በቆሰሉና በደሙ ጊዜ ያለስራ ትቀመጣላ ችሁን?

፳፫ አሁንም ተቀምጣችሁ እነዚህን ነገ ሮች በምትመለከቱበት ጊዜ እግዚአብሔር እንከን የሌላችሁ አድርጎ ይቆጥረናል ብላ ችሁ ትገምታላችሁን? እነሆ እኔ ግን እን ደዚህ አድርጎ አይቆጥራችሁም እላለሁ። እንግዲህ የመያዣው ᵐእቃ ውስጥ በመጀ መሪያ እንዲጠራ፣ እናም ደግሞ የእቃው ውጭ እንዲጠራ እግዚአብሔር መናገሩን እንዲያስተውሉ እፈልጋለሁ።

፳፬ እናም እንግዲህ፣ ለሰራችሁት ስራ ንስሃ ካልገባችሁና፣ በስራችሁ ንቁ ካልሆ ናችሁ፣ እንዲሁም በድጋሚ ያገኛትን የሀገ ራችንን ክፍል ይደግፉት ዘንድና፣ ምና ልባት ደግሞ በዚህኛው ክፍል የተቀረ ውን ንብረታችንን እናገኝ ዘንድ፣ እናም ወደ እኛምና፣ ደግሞ ለሌለማን፣ ምግ ብና ሰው ካልላካችሁ፤ እነሆ የውስጥ መያ ዣችንን እቃ፣ አዎን የመንግስታችን የበ ላይ ሹማምንቶችንም ቢሆን፣ እስከምና ጠራ ከላማናውያን ጋር መጣላቱ አስፈላጊ አይደለም።

፳፭ እናም የደብዳቤዬን መልስ ካልሰ ጠኸኝ በቀር፣ እናም ወጥተህና እውነተኛ ውን ᵐየነፃነት መንፈስ ካላሳየኸኝና፣ ወታ ደሮቻችንን ካላበረታህና ካላጠናከርህና፣ ለድጋፋቸው ምግብ ካልሰጠኻቸው እነሆ የነፃነት ሰዎቼን ይህንን ክፍል እንዲያስተ ዳድሩ እተዋቸዋለሁ፤ እናም ሌላ ኃይል በእነርሱ ላይ መስራት እንዳይችል የእግዚ አብሔርን ብርታትና በረከት በእነርሱ ላይ አደርጋለሁ—

፳፮ እናም ይህን የማደርገው በታላቁ እም ነታቸው፣ እናም በመከራቸው ጊዜ በነበራ ቸው ትዕግስት ነው—

፳፯ እናም ወደ እናንተ እመጣለሁና፣ በመካከላችሁ ነፃነት የሚፈልግ ቢኖር፣ አዎን፣ የቀረም የነፃነት ብልጭታ ቢኖር፣ እነሆ፣ ኃይልና ስልጣንን ያለአግባብ በመ ካከላችሁ የሚያነሳሱት እንኳን እስከሚጠፉ ድረስ አመፅ አስነሳለሁ።

፳፰ አዎን፣ እነሆ ኃይላችሁንም ሆነ ስል ጣናችሁን አልፈራም፤ ነገር ግን ᵐአም ላኬን ነው የምፈራው፤ እናም እንደትዕ ዛዛቱ ሀገሬን ለመከላከል ጎራዴዬን አነሳ ለሁ፤ እናም በክፋታችሁ የተነሳ ነው ብዙ ዎች የጠፉት።

፳፱ እነሆ ይህ ጊዜው ነው፤ አዎን አሁን ጊዜው ደርሷል፣ ራሳችሁን፣ ሀገራችሁ ንና፣ ልጆቻችሁን ለመከላከል ካላነሳሳችሁ የፍትህ ᵐጎራዴ በእናንተ ላይ ይንዣባለላል፤ አዎን፣ እናም በእናንተ ላይ ይሆናል፣ እን ዲሁም ፈፅሞም ለጥፋታችሁ ይሆናል።

፴ እነሆ፣ ከእናንተ እርዳታን እጠብቃ

ᵐ ሀ ማቴ. ፳፫፡፳፭–፳፮። ᵐ ሀ የሐዋ. ፭፡፳፮–፳፱።
ᵐ ሀ አልማ ፶፭፡፮፣ ፳፭፡፲፭። ᵐ ሀ ሔለ. ፲፫፡፭፣ ፲ ኔፊ ፪፡፲፱።

ለሁ፤ እናም፣ እርዳታችንን እንድናገኝ ካልሰራችሁ በቀር፣ እነሆ፣ ወደ ዛራሔምላ ምድርም እንኳን እመጣለሁና፣ ለነፃነታ ችን መንስኤ የዚህን ህዝብ እድገት ለማገድ ስልጣን ከዚህ ወዲያ ሊኖርህ እስከማይችል ድረስ በጎራዴ እመታሃለሁ።

፴፩ እነሆም፣ ጌታ እንድትኖር፣ እናም ፃድቅ ህዝቡን ለማጥፋት በክፋትህ እንድ ትጠነክር አይፈቅድልህም።

፴፪ እነሆ ክፋትህ ክብርህን እና የዓለምን ከንቱ ነገሮች ለመውደድ ሆኖ እያለ፣ ጌታ በአባቶቻቸው ወግ ምክንያት ጥላቻ ያላቸ ውን፣ አዎን እናም ይኸውም ከእኛ በተገነ ጠሉት ላይ በተጨመረባቸው ላማናውያን ላይ ጌታ በፍርድ እንደሚመጣባቸውና፣ ራሳችሁን ያድናችኋል ብላችሁ ትገምታ ላችሁን?

፴፫ የእግዚአብሔርን ህግጋት መተላለ ፍህን ታውቃለህ፣ እናም እነዚህን በእግ ርህ መርገጥህንም ታውቃለህ። እነሆ ጌታ እንዲህ ብሎኛል፥ ገዢ አድርገህ የሾምካ ቸው ለኃጢአታቸው እና ለክፋታቸው ንስሃ ካልገቡ ከእነርሱ ጋር ሄደህ መዋጋት ይኖ ርብሃል።

፴፬ እናም እንግዲህ እነሆ፣ እኔ፣ ሞሮኒ፣ የአምላኬን ትዕዛዛት ለመጠበቅ በገባሁት ቃል ኪዳን መሰረት እገፋፋለሁ፤ ስለዚህ የእግዚአብሔርን ቃል እንድትቀበሉ እፈ ልጋለሁ፣ እናም ከቀለባችሁና፣ ከሰዎቻ ችሁ ላኩልኝ፣ እናም ደግሞ ለሔለማን በፍ ጥነት ላኩለት።

፴፭ እናም እነሆ ይህንን የማታደርጉ ከሆነ በፍጥነት ወደ እናንተ እመጣለሁ፤ እነሆም፣ እግዚአብሔር በረሃብ እንድንጠፋ አይፈ ቅድም፤ ስለዚህ በጎራዴም ቢሆን ከምግባ ችሁ ይሰጠናል። እንግዲህ የእግዚአብሔ ርን ቃል ፈፅሙ።

፴፮ እነሆ፣ እኔ ሊቀ ሻምባል ሞሮኒ ነኝ። ፍላጎቴ [a]ለስልጣን ሳይሆን፣ ነገር ግን ይህን ጎትቶ ለማውረድ ነው። የዓለምን ክብር ሳይሆን፣ የአምላኬ ክብርን እናም የሀገሬን ነፃነትና ደህንነት ነው የምፈልገው። እናም ደብዳቤዬን አበቃለሁ።

ምዕራፍ ፰፩

ፓሆራን በመንግስት ላይ ስለሆነው ሁከት፣ እና አመፃ ለሞሮኒ ነገረው—የንጉሱ ሰዎች ዛራሔምላን ያዙ፣ እናም ከላማናውያን ጋር አንድ ቡድን ሆኑ—ፓሆራን በአ ማፅያኑ ላይ ወታደራዊ እርዳታን ጠየቀ። በ፰፪ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እነሆ እንዲህ ሆነ ሞሮኒ ለዋናው ገዢ ደብዳቤውን ከላከ በኋላ፣ ወዲያውኑ ከዋናው ገዢ [a]ፓሆራን ደብዳቤ ደረሰው። እናም የተቀበለው ቃል እንዲህ ይላል፥

፪ እኔ ፓሆራን የዚህች ምድር ዋና ገዢ የሆንኩ፣ በሠራዊቱ ሊቀ ሻምባል ለሆ ነው ሞሮኒ ይህንን መልዕክት ልኬአለሁ። እነሆ፣ ሞሮኒ እልሀለሁኝ፣ በታላቁ [a]ስቃ ይህ አልደሰትም፤ አዎን፣ ይህ ነፍሴን ያሳ ዝናታል።

፫ ነገር ግን እነሆ፣ በስቃይህ የሚደሰቱት አሉ፣ አዎን፣ በእኔ እናም [a]የነጻነት ሰዎች በሆኑት ህዝቦቼ ላይ በአመፅ ተነስተዋል፣ አዎን፣ ለአመፅ የተነሱት በቁጥር እጅግ ብዙ ናቸው።

፬ እናም የፍርዱን ወንበር ከእኔ ለመው ሰድ የፈለጉት የዚህ የታላቁ ክፋት መንስኤ ናቸው፤ ምክንያቱም ታላቅ የሽንገላ ቃላት ተጠቅመዋል፣ እናም በመካከላችን የአደገኛ ስቃይ መንስኤ እንዲሆን የብዙዎችን ልብ ለውጠዋል፤ ስንቆቻችንን ይዘውብናልና፣ ወደ አንተም እንዳይመጡ ነፃ የሆኑትን ሰዎ ቻችንን አስፈራርተውብናል።

፭ እናም እነሆ፣ ከፊታቸው እኔንም አባ ረውኛል፣ እናም ከእኔጋ ለማግኘት ከምች ላቸው ያህል ሰዎች ጋርም ወደ ጌዴዎን ምድር ሸሽቻለሁ።

፮ እናም እነሆ፣ በዚች ምድር አዋጅ ልኬ

---

[a]፴፮ ሆ ት.እና ቃ. የ፰፩፡ ፴፱–፴፪። [a]፪ ሆ አልማ ፰፡ ፫–፱። [a]፰ ሆ አልማ ፱፡ ፴–፴፡ [a]፰ ሆ አልማ ፱፡ ፴–፴፡ [a]፫ ሆ አልማ ፱፡ ፮–፯።

አለሁ፤ እናም እነሆ ሀገራቸውንና ᵐነፃነታ ቸውን ለመከላከልና፣ ስህተቶቻችንንም ለመበቀል የጦር መሳሪያቸውን ለማንሳት በየቀኑ ወደእኛ ይሰበሰባሉ።

፲ እናም በእኛ ላይ ለአመፅ የተነሱት፣ አዎን፣ እነርሱ እስከሚፈሩን፣ እናም ለውጊያ በእኛ ላይ ለመምጣት እስከማይ ደፍሩም ድረስ ወደ እኛ መጥተዋል።

፲፩ ምድሪቱን እንዲሁም የዛራሔምላ ከተማን ይዘዋል፤ በእነርሱም ላይ ንጉሥን ሹመዋል፣ እናም ለላማናውያን ንጉስም ጽፏል፣ በዚህም ከእርሱ ጋር አንድነት ኖሯቸዋል፤ በዚህም አንድነት የዛራሔም ላን ከተማ ለማስተዳደር ተስማማ፤ በሚ ያስተዳድርበት ጊዜም ላማናውያን የተቀ ረውን ምድር ያሸንፋሉ፤ እናም በላማና ውያን በተሸነፉ ጊዜም በህዝቡ ላይ ንጉስ በመሆንም ይሾማል በማለት ገምቶ ነበር።

፲፪ እናም እንግዲህ፣ በደብዳቤህ ላይ ወቅ ሰኸኛል፣ ነገር ግን ይህ ምንም አይደለም፣ እኔም አልተቆጣሁም፣ ነገር ግን ከልብህ ታላቅነት ተደስቻለሁ። እኔ ፓሆራን የህ ዝቤን መብትና ነፃነት የምጠብቅበትን የፍ ርድ ወንበሬን ብቻ ከመመለስ በቀር ስልጣ ንን አልፈልግም። እግዚአብሔር ᵐነፃ ባደረ ገን በዚያ ነፃነት ህይወቴ ትፀናለች።

፲፫ እናም እንግዲህ፣ እነሆ፣ ኃጢያትን ደም እስከሚፈስ ድረስ እንቃወማለን። ላማናውያን በምድራቸው የሚቆዩ ከሆነ ደማቸውን አናፈሰውም።

፲፬ ወንድሞቻችን በአመፅ ካልተነሳሱ፣ እናም ጎራዴአቸውን በእኛ ላይ ካላነሱ ደማ ቸውን አናፈስም።

፲፭ በእግዚአብሔር ፍርድ አስፈላጊ ከሆነ እንዲሁም እርሱ እንድናደርገው ካዘዘን እራሳችንን በባርነት ቀንበር ስር ማድረግ ይኖርብናል።

፲፮ ነገር ግን እነሆ እግዚአብሔር እራሳች ንን በጠላቶቻችን ስር እንድናደርግ አያዘ ንም፤ ነገር ግን ᵐእምነታችንን በእርሱ ላይ ማድረግ አለብን፣ እናም እርሱ ያድነናል።

፲፯ ስለዚህ፣ የተወደድክ ወንድሜ፣ ሞሮኒ፣ ክፋትን እንቃወም፣ እናም በቃል ለመቃወም የማንችላቸውን ክፉቶችን፣ አዎን፣ እንደሚያምጹትና ከእኛ እንደ ሚገነጠሉት አይነት፣ ነፃነታችንን እና ገኝ ዘንድ፣ በቤተክርስቲያን ታላቅ ጥቅም እናም በአዳኛችንና በአምላካችን እንደሰት ዘንድ፣ እነርሱን በጎራዴዎቻችን ᵐእንቃ ወማቸው።

፲፰ ስለዚህ፣ ከጥቂት ሰዎችህ ጋር በፍ ጥነት ወደ እኔ ና፣ እናም የቀሩትን በሌ ሂና በቴአንኩም ትዕዛዝ ስር እንዲሆኑ ተዋ ቸው፤ ᵐበእግዚአብሔር መንፈስ መሰረት፣ ደግሞም በእነርሱ ውስጥ ባለው የነፃነት መንፈስ በዚያ ምድር ጦርነቱን እንዲመሩ ስልጣንን ስጣቸው።

፲፱ እነሆ አንተ ወደ እኔ እስከምትመጣ ድረስ እንዳይጠፉ ጥቂት ስንቅ ልኬላቸ ዋለሁ።

፲፳ ወደዚህ ስፍራ ለዘመቻህ ያለህን ኃይል በሙሉ በአንድነት አሰባስብ፤ እናም በአም ላካችን ባለን እምነት በኃይል በተቃዋሚ ዎቹ ላይ በፍጥነት እንሄዳለን።

፲፳፩ እናም ወደ ሌሂና ቴአንኩም ለመላክ ተጨማሪ ስንቅ እናገኝ ዘንድ የዛራሔምላን ከተማ እንወስዳለን፤ አዎን፣ በጌታ ኃይ ልም በእነርሱ ላይ እንሄዳለን፣ እናም ለዚህ ታላቅ ጥፋትም ፍፃሜ እንዲሆን እናደር ጋለን።

፲፳፪ እናም እንግዲህ፣ ሞሮኒ፣ በወንድሞ ቻችን ላይ መዝመት ትክክል ይሁን አይሁን ምን ማድረግ እንዳለብኝ በመጠኑ ተጨንቄ ስለነበር፣ ደብዳቤህን በማግኘቴ ተደስቻ ለሁ።

፲፳፫ ነገር ግን ንስሃ ካልገቡ በእነርሱ ላይ መሄድ አለባችሁ በማለት ጌታ እንዳዘዘህ ተናግረሃል።

፲፮ ሀ ቅ.መ.መ. መብት፤ ነጻ፣ ነጻነት።
፲፱ ሀ ዮሐ. ፲፡ ፴፩–፴፮፤ ᵐ ትና ቃ. ፹፰፡ ፹፮።
፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. መታመን፤ እምነት፣ ማመን።
፲፴ ሀ አልማ ፴፫፡ ፴፯።
፲፭ ሀ ᵐ ቆሮ. ፫፡ ፲፯።
ᵐ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።

፰፭ የሌሂንና፣ ቴአንኩምን እምነት ᵐማጠ ናከርን አረጋግጥ፤ እንዳይፈሩ ንገራቸው፤ እነርሱን፤ አዎን፣ እናም ደግሞ እግዚአብ ሔር ባደረጋቸው ነፃነት የሚጸኑትን ያድ ናልና። እናም እንግዲህ ለተወደደው ወን ድሜ ሞሮኒ ደብዳቤዬን አበቃለሁ።

ምዕራፍ ፰፪

ሞሮኒ ፓሆራንን ለመርዳት ወደ ጌዴ ዎን ምድር ዘመተ—ሀገራቸውን ለመከ ላከል የተቃወሙት የንጉስ ሰዎች ተገድ ለዋል—ፓሆራን እናም ሞሮኒ ኔፋውያ ንን በድጋሚ ያዙ—ብዙ ላማናውያን ከአ ሞንን ሰዎች ጋር ተቀላቀሉ—ቴአንኩም አሞሮንን ገደለው እናም ቀጥሎም እራሱ ተገደለ—ላማናውያን ከምድሪቱ ተባረሩ፣ እናም ሰላም ሠፈነ—ሔለማን ወደ አገል ግሎቱ ተመለሰ፣ እናም ቤተክርስቲያኗን አሳደገ። ከ፰፪–፻፲ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንግዲህ እንዲህ ሆነ ሞሮኒ ይህ ንን ደብዳቤ በተቀበለ ጊዜ ስሜቱ ተነሳስቶ ነበር፣ እናም በፓሆራን ታማኝነት፣ ደግ ሞም ለሀገሩ ነፃነት ᵐከሀዲ ስላልነበረ በታ ላቅ ደስታ ተሞልቶ ነበር።

፪ ነገር ግን ፓሆራንን ከፍርድ ወንበር ባባረሩት ኃጢያትም ደግሞ እጅግ አዝኖ ነበር፤ አዎን፣ በአጠቃላይ በሀገራቸው ላይ እናም ደግሞ በአምላካቸው ላይ ባመፁት አዝኖ ነበር።

፫ እናም እንዲህ ሆነ እንደ ፓሆራን ፍላ ጎት ሞሮኒ ጥቂት ሰዎችን ወሰደ፤ እናም ለሌሂና፣ ቴአንኩም በቀሪዎቹ ወታደሮች ላይ አዛዥ አደረጋቸው፤ ጉዞውንም ወደ ጌዴዎን ምድር አደረገ።

፬ እናም በደረሰበት ስፍራ ሁሉ ᵐየነፃ ነት ᵃአርማውን አነሳ፣ እናም ወደ ጌዴ ዎን ምድር በዘመተበት ሁሉ የሚችለውን ኃይል አገኘ።

፭ እናም እንዲህ ሆነ በሺህ የሚቆጠሩ ወደ አርማው በአንድነት ተሰበሰቡ፣ እናም በባ ርነት ስር እንዳይወድቁ ለነፃነታቸው ለመ ታገል ጎራዴያቸውን አነሱ።

፮ እናም ሞሮኒ የሚችለውን ሁሉ ሰው በአንድነት በሰበሰበ ጊዜ፣ ወደ ጌዴዎን ምድር መጣ፤ እናም ጠንካራ ከሆኑት ከፓሆራን ወታደሮችም ጋር ቀላቀላቸው፣ እነርሱም ከዛራሔምላ ምድር ᵐነፃ የሆኑትን ሰዎች ካስወጡት ከተቃዋሚዎች ᵃንጉስ፣ እናም ምድሪቱን ከወሰደው ከፓኩስ የበ ለጠ ጠንካሮች ሆኑ።

፯ እናም እንዲህ ሆነ ሞሮኒና ፓሆራን ከወታደሮቻቸው ጋር ወደ ዛራሔምላ ምድር ሄዱ፣ እናም ከተማዋን አጠቁና፣ ለውጊያም የፓኩስን ሰዎች አገኙአቸው።

፰ እናም እነሆ፣ ፓኩስ ተገደለና የእ ርሱም ሰዎች እስረኞች ሆነው ተወሰዱ፣ እናም ፓሆራን ወደ ፍርድ ወንበሩ ተመ ለሰ።

፱ እናም በህጉ መሰረት የፓኩስ ሰዎች፣ እናም ደግሞ በምርኮ ተወስደው ወህኒ ቤት የተጣሉት የንጉስ ሰዎች በህጉ መሰረት ᵐተገደሉ፤ አዎን፣ ሀገራቸውን ለመከላ ከል የጦር መሳሪያ ያልያዙት ሁሉ፣ ነገር ግን ይህንን በመቃወም የተዋጉት፣ አዎን፣ የፓኩስና የንጉስ ሰዎች፣ እንዲገደሉ ተደ ረገ።

፲ እናም ይህን ህግ ለሀገራቸው ደህንነት ሲባል በጥብቅ መከተሉ እንደዚህ አስፈ ላጊ ሆነ፤ አዎን፣ እናም ነፃነታቸውን ሲክድ የተገኘ ማንኛውም በህጉ መሰረት በፍጥነት ይገደል ነበር።

፲፩ እናም እንደዚህ በኔፊ ህዝብ ላይ የመ ሣፍንቱ ሰላሳኛ የንግስ ዘመን ተፈፀመ፤ ሞሮኒ እናም ፓሆራን በዛራሔምላ ምድር በህዝባቸው መካከል ለነፃነታቸው ምክን ያት ታማኝ ባልሆኑት ላይ ሁሉ የሞት ፍርድ በመፍረድ ሰላምን መሠረቱ።

፰፭ *ሀ* ዘካ. ፲፡ ፲፪።
፰፪ ፩ *ሀ* አልማ ፰፡ ፲፰።
፪ *ሀ* ቅ.መ.መ. መብት።
ለ አልማ ፻፯፡ ፲፪–፲፫፣ ፴፯።
ቅ.መ.መ. ምልክት።
፯ *ሀ* አልማ ፻፴፡ ፭–፯።
ለ አልማ ፰፭፡ ፪–፰።
፱ *ሀ* ቅ.መ.መ. የሞት ቅጣት።

፲፪ እናም እንዲህ ሆነ በኔፊ ህዝብ ላይ በመሣፍንቱ ሰላሳ አንደኛ የንግስና ዘመን መጀምሪያ ላይ፣ ሞሮኒ ምግብ በፍጥነት እንዲላክ፣ እናም ደግሞ ስድስት ሺህ ወታ ደሮች ሒለማንን ምድሪቱን ለመጠበቅ እን ዲረዱት ዘንድ እንዲላኩ አዘዘ።

፲፫ እናም ደግሞ ስድስት ሺህ የሚጠጉ ሰዎች ከበቂ ምግብ ጋር ወደ ሌሂና ቴአን ኩም ወታደሮች እንዲላኩ አደረገ። እናም እንዲህ ሆነ ይህም የተደረገው ምድሪቱን ከላማናውያን ለመጠበቅ ነበር።

፲፬ እናም እንዲህ ሆነ ሞሮኒና ፓሆራን በዛራሔምላ ምድር ብዙ ቁጥር ያላቸውን ሰዎች በመተው፣ ላማናውያንን በዚያች ከተማ ለማሸነፍ በመቁረጥ ወደ ኔፋውያን ምድር ጉዞአቸውን አደረጉ።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ ወደ ምድሪቱ በዘ መቱ ጊዜ ከላማናውያን በርካታ ሰዎችን ያዙና፣ ብዙዎቹን ገደሉ፣ እናም ስንቃቸው ንና የጦር መሳሪያዎቻቸውን ወሰዱባቸው።

፲፮ እናም እንዲህ ሆነ ሞሮኒ፣ እነርሱን ከወሰዱ በኋላ፣ በኔፋውያን ላይ በድጋሚ የጦር መሳሪያዎቻቸውን እንዳያነሱ ቃል ኪዳን እንዲገቡ አደረጉአቸው።

፲፯ እናም ይህንን ቃል ኪዳን በገቡም ጊዜ ከአሞን ህዝብ ጋር እንዲኖሩ ላኩአቸው፤ እናም ያልሞቱት ቁጥር ወደ አራት ሺህ ይጠጋ ነበር።

፲፰ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያንን በላ ኩአቸው ጊዜ ጉዞአቸውን ወደ ኔፊአያህ ምድር ቀጠሉ። እናም እንዲህ ሆነ ወደ ኒፋአያህ ከተማ በመጡ ጊዜም፣ በኒፋአ ያህ ከተማ አጠገብ በሜዳው ላይ ድንኳና ቸውን ተከሉ።

፲፱ እንግዲህ ሞሮኒ በሜዳው ላይ ላማና ውያን መጥተው እንዲዋጉ ፈልጎ ነበር፤ ነገር ግን ላማናውያን ያላቸውን ታላቅ ድፍ ረት በማወቃቸው፣ እናም በቁጥር እጅግ ብዙ መሆናቸውን ተመለከቱ፣ ስለዚህ በእ ነርሱ ላይ ለመምጣት አልደፈሩም፤ ስለ ዚህ በዚያን ቀን ለውጊያ አልመጡም ነበር።

፳ እናም ምሽቱ በመጣም ጊዜ፣ ሞሮኒ በምሽት ጨለማ ሄደ፣ እናም በግንቡ ጫፍ ላይ ላማናውያን ከወታደሮቻቸው ጋር የጦር ምሽግ ያደረጉበትን ከተማ በስለላ ለማየት ሄደ።

፳፩ እናም እንዲህ ሆነ በመግቢያው በኩል በስተምስራቅ ነበሩ፣ እናም ሁሉም ተኝ ተው ነበር። እናም አሁን ሞሮኒ ወደ ወታ ደሮቹ ተመለሰና፣ ከግንቡ ጫፍ ወደ ውስጥ እንዲሆኑም ለማድረግ በፍጥነት ጠንካራ ገመድ እንዲሁም መሰላል እንዲያዘጋጁ አደረገ።

፳፪ እናም እንዲህ ሆነ ሞሮኒ የእርሱ የሆ ኑት ሰዎች እንዲሄዱ፣ እናም በግንቡ ጫፍ እንዲመጡ፣ እንዲሁም ወደ ከተማዋ፣ አዎን፣ በስተምዕራብ በኩልም እንኳን ላማናውያን ከወታደሮቻቸው ጋር ወዳል ሰፈሩበትም እንዲወርዱ አደረገ።

፳፫ እናም እንዲህ ሆነ በጠንካራው ገመ ድና፣ መሰላል አማካኝነት በምሽት ሁሉም ወደ ከተማዋ ገቡ፤ ጠዋት በሆነም ጊዜ ሁሉም በከተማዋ ግንብ ውስጥ ነበሩ።

፳፬ እናም እንግዲህ፣ ላማናውያን በተ ነሱ ጊዜና የሞሮኒ ወታደሮች በግንቡ ውስጥ መሆናቸውን በተመለከቱ ጊዜ በበሩም ሸሽ ተው እስከሚወጡ ድረስ እጅግ ፈርተው ነበር።

፳፭ እናም አሁን ሞሮኒ ከፊቱ መሸሻቸ ውን በተመለከተ ጊዜ፣ የእርሱ ሰዎች በእ ነርሱ ላይ እንዲዘምቱ አደረገና፣ ብዙዎችን ገደሉ፣ እናም ሌሎች ብዙዎችን ከበቡአ ቸው፣ እናም በእስረኛነት ወሰዱአቸው፤ እናም የተቀሩት በባህሩ ዳርቻ ወደነበረው ወደ ሞሮኒ ምድር ሸሹ።

፳፮ ሞሮኒ፣ እናም ፓሆራን አንድም ነፍስ ሳይጠፋባቸው የኒፋአያህን ከተማ እንዲህ ወሰዱ፤ እናም የተገደሉ ብዙ ላማናውያን ነበሩ።

፳፯ እንግዲህ እንዲህ ሆነ እስረኞች የነበሩ ብዙ ላማናውያን [ሀ]ከአሞን ሰዎች ጋር ለመ ገናኘት፣ እናም ነፃ ሰው ለመሆን ፈለጉ።

፳፯ ሀ ቅ.መ.መ. አንቲ-ኔፊ-ሌሂ።

፰፰ እናም እንዲህ ሆነ ብዙዎች እንደፍላጎታቸው ተደርጎላቸዋል።

፰፱ ስለዚህ የላማናውያን እስረኞች በሙሉ የአሞን ህዝቦች አባል ሆኑ፣ እናም ተግተው መስራት፣ መሬት ማረስ፣ ሁሉንም ዓይነት እህል መዝራትና፣ ሁሉንም ዓይነት ከብቶችና፣ መንጋዎች ማርባት ጀመሩ፤ እናም እንደዚህ ኔፋውያን ከታላቁ ሽክማቸው አረፉ፤ አዎን ከላማናውያን እስረኞች በሙሉ ተላቀቁ።

፱ እንግዲህ እንዲህ ሆነ፣ ሞሮኒ የኒፋአያህን ከተማ ካገኘ በኋላ፣ የላማናውያን ወታደሮችን የቀነሱአቸውን ብዙ እስረኞችንም ከወሰደ በኋላ፣ እናም እስረኞች ተደርገው የተወሰዱትን ኔፋውያንን ብዙዎችን በድጋሚ ስላገኙ የሞሮኒን ወታደሮች ተጠና ከሩ፤ ስለዚህ ሞሮኒ ከኒፋአያህ ከተማ ወደ ሌሂ ምድር ሄደ።

፱፩ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን ሞሮኒ በእነርሱ ላይ መምጣቱን በተመለከቱ ጊዜ፣ በድጋሚ ፈሩ፣ እናም ከሞሮኒ ወታደሮች ፊት ሸሹ።

፱፪ እናም እንዲህ ሆነ ሞሮኒና ሠራዊቱ ከሌሂና ከቴአንኩም ጋር እስከሚያገኙአቸው ድረስ ከአንዱ ከተማ ወደ ሌላኛው ተከተሉአቸው፤ እናም ላማናውያን ከሌሂና ከቴአንኩም በባህሩ ዳርቻ ወደ ሞሮኒ ምድር እስከሚመጡ ድረስ ሸሹ።

፱፫ እናም የላማናውያን ሠራዊቶች በሞሮኒ ምድር አንድ እስከሚሆኑ ድረስ ሁሉም በአንድነት ተሰበሰቡ። አሁን አሞሮን፣ የላማናውያን ንጉስም ደግሞ ከእነርሱ ጋር ነበር።

፱፬ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን በምድረበዳው በስተደቡብና፣ በምድረበዳው በስተምስራቅ እስከሚከበቡ ድረስ፣ ሞሮኒና፣ ሌሂ፣ እናም ቴአንኩም በሞሮኒ ምድር ዳርቻ ዙሪያ ከወታደሮቻቸው ጋር ሰፈሩ።

፱፭ እናም በምሽት እንደዚህ ሰፈሩ። እነሆም፣ ኔፋውያንና፣ ደግሞ ላማናውያን በጉዞው ታላቅነት ምክንያት ደክሞአቸው ነበር፤ ስለዚህ ከቴአንኩም በስተቀር በምሽት ምንም ዓይነት የጦር ስልት አልወሰኑም ነበር፤ ምክንያቱም እርሱ በአሞሮን እጅግ ተቆጥቶ ነበር፤ ምክንያቱም አሞሮንና ወንድሙ አማሊቅያ ይህ ታላቅና፣ መጨረሻ የሌለው ጦርነት በእነርሱና በላማናውያን መካከል ለተደረገው፣ ለረጅሙ ጦርነትና፣ ደም መፋሰስ አዎን እናም ለከፋ ረሃብ ᵘመንስኤ መሆናቸውን ስላሰበ ነበር።

፱፮ እናም እንዲህ ሆነ ቴአንኩም በቁጣ ወደ ላማናውያን የጦር ሰፈር ሄደ፤ በከተማዋ ግንብ ውስጥም ገባ። እናም ከቦታ ቦታ በገመድ ሄዶ ንጉሱን አገኘው፤ በእርሱም ላይ ጦር ᵘወረወረበት፣ እርሱም በልቡ አጠገብ ወጋው። ነገር ግን እነሆ ንጉሱ ከመሞቱ በፊት አገልጋዮቹን ቀሰቀሳቸው፣ እነርሱም ቴአንኩምን ተከተሉት፣ እናም ገደሉት።

፱፯ እንግዲህ እንዲህ ሆነ ሌሂና ሞሮኒ ቴአንኩም መሞቱን ባወቁ ጊዜ እጅግ አዝነው ነበር፤ እነሆ እርሱ ለሀገሩ በጥንካሬ የተዋጋ፣ አዎን፣ ለነፃነት እውነተኛ ጓደኛ የሆነ ሰው ነበር፤ እናም በብዙ አሰቃቂ ስቃይ እጅግ ተሰቃይቶ ነበር። ነገር ግን እነሆ ሞተ፣ እናም ምድር ሁሉ ወደሚሄዱበት ሄዷል።

፱፰ እንግዲህ እንዲህ ሆነ ሞሮኒ በሚቀጥለው ቀን ዘመተና፣ በታላቅ ሁኔታ እስከሚገድሏቸው ድረስ ወደ ላማናውያን መጡ፤ እናም ከምድሪቱ አባረሩአቸው፤ እናም ሸሹ፣ እንዲሁም በዚያን ጊዜ በኔፋውያን ላይ አልተመለሱም።

፱፱ እናም በኔፊ ህዝብ ላይ የመሣፍንቱ ሰላሳ አንደኛ የንግሥና ዘመን ተፈፀመ፤ እናም ለብዙ አመታት ጦርነትና፣ ደም መፋሰስ፣ እናም ረሃብና፣ ስቃይ ነበራቸው።

፲ እናም በኔፊ ሰዎች መካከል ግድያና፣ ፀብና፣ መከፋፈል፣ እንዲሁምም ሁሉም ዓይነት ክፋት ነበር፤ ይሁን እንጂ ᵘለፃድቃኖች ሲባል፣ አዎን፣ በፃድቃኖች ፀሎትም ምክንያት እነርሱ ድነዋል።

፴፩ ነገር ግን እነሆ፣ በኔፋውያንና በላ
ማናውያን መካከል በነበረው ታላቅ ጦር
ነት እርዝማኔና ጦርነቱ እጅግ ረጅም በመ
ሆኑ ብዙዎች ጠጣሮች ሆኑ፤ እናም ብዙ
ዎች ᵐበስቃያቸው የተነሳ በእግዚአብሔር
ፊት እራሳቸውን እስከሚያዋርዱ፣ በጥ
ልቅ ትህትናም ዝቅ እስከሚሉ ለስላሶች
ነበሩ።

፴፪ እናም እንዲህ ሆነ ለላማናውያን ይበ
ልጥ የተጋለጠውን ምድር በብቁ ጠን
ካራ እስኪሆኑ ድረስ ሞሮኒ ምሽግ ካደረገ
በኋላ፣ ወደ ዛራሔምላ ምድር ተመለሰ፤
እናም ደግሞ ሔለማን ወደ ትውልድ ስፍ
ራው ተመለሰ፤ እናም በኔፊ ህዝብ መካከል
እንግዲህ ሰላም ተመሰረተ።

፴፫ እናም ሞሮኒ ሞሮኒሀ ተብሎ ለሚ
ጠራው ልጁ የሠራዊቱን መሪነት አሳልፎ
ሠጠ፤ እናም ቀሪውን ጊዜውን በሰላም ያሳ
ልፍ ዘንድ በቤቱ ተቀመጠ።

፴፬ እናም ፓሆራን ወደፍርድ ወንበሩ
ተመለሰ፤ እናም ሔለማን ለህዝቡ የእግዚ
አብሔርን ቃል ለመስበክ ሀላፊነትን ተቀ
በለ፤ ብዙ ጦርነቶችና ፀብ ስለነበሩ በቤተ
ክርስቲያኗ በድጋሚ ደንብ ማውጣት አስ
ፈላጊ ሆኖ ነበር።

፴፭ ስለዚህ፣ ሔለማንና ወንድሞቹ
ሄዱና፣ የእግዚአብሔርን ቃል ብዙ ኃጢ
አተኞችን ᵐለማሳመን ተናገሩ፤ ብዙዎች
ንም ለኃጢአታቸው ንስሃ እንዲገቡ፣ እናም
በጌታ በአምላካቸው እንዲጠመቁ አደረ
ጓቸው።

፴፮ እናም እንዲህ ሆነ በምድሪቱ ሁሉ
በድጋሚ የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን
አቋቋሙ።

፴፯ አዎን፣ እናም ህጉን በተመለከተ
ደንብ ወጣ። እናም ᵐዳኞቻቸውንና፣ ዋና
ዳኞቻቸውን ተመረጡ።

፴፰ እናም የኔፊ ህዝብ በምድሪቱ ላይ
በድጋሚ ᵐመበልፀግ ጀመሩና፣ በድጋሚ
በምድሪቱ ተባዙና እጅግ ጨመሩ። እናም
እጅግ ሀብታም መሆን ጀመሩ።

፴፱ ነገር ግን ሀብታም እንዲሁም ጠን
ካሮች፣ እናም የበለፀጉ ቢሆኑም በኩራት
ከፍ ብለው አልታዩም፤ ወይም ጌታ አም
ላካቸውንም ለማስታወስ አልዘገዩም፤ ነገር
ግን በፊቱ እራሳቸውን እጅግ አዋርደው
ነበር።

፴ አዎን፣ ጌታ ታላላቅ ነገሮችን እን
ዴት እንዳደረገላቸው፣ ከሞትና፣ ከባር
ነት፣ እናም ከእስርና፣ ከሁሉም ዓይነት
ስቃይ እንዳዳናቸው፣ እናም ከጠላቶቻ
ቸው እጅም እንዴት እንዳስለቀቃቸው
ያስታውሱ ነበር።

፴፩ እናም እንደቃሉ ጌታ እስከሚባርካ
ቸው ወደ ጌታ አምላካቸው ሳያቋርጡ ይፀ
ልዩ ነበር፣ ስለዚህ በምድሪቱ ላይ በረቱም
በለፀጉም።

፴፪ እናም እንዲህ ሆነ እነዚህ ነገሮች ሁሉ
ተፈፀሙ። እናም ሔለማን በኔፊ ህዝብ ላይ
በመሣፍንቱ ሰላሳ አምስተኛ የንግስ ዘመን
ሞተ።

ምዕራፍ ፰፫

ሺብሎን እናም በኋላ ሔለማን ቅዱሳን መፃሕፍቶቹን ወሰዱ—በርካታ ኔፋውያን ወደ ሰሜኑ ምድር ተጓዙ—ሐጋዝ በባህ ሩም በስተምዕራብ በኩል የሔዱትን መር ከቦች ሰራ—ሞሮኒሀ ላማናውያንን በውጊያ አሸነፋቸው። ከ፳፯–፳፪ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ በኔፊ ህዝብ ላይ
በመሣፍንቱ ሰላሳ ስድስተኛ ዓመት የንግ
ስና ዘመን በአልማ ለሔለማን የተሰጡትን
ᵐቅዱሳን ነገሮችን ᵃሺብሎን ተረከባቸው።

፪ ሺብሎንም ፃድቅ ሰው ነበር፣ እናም
በእግዚአብሔር ፊትም በቅንነት ይራመድ
ነበር፤ እናም ያለማቋረጥ እርሱም፣ ደግሞ
ወንድሙም፣ መልካም ለመስራት የጌታ

፴፩ ሀ ቅ.መ.መ. ጭንቀት።
፴፩ ለ ት.እና ቃ. ፲፰፡፴፩።
፴፪ ሀ ሞዛያ ፳፱፡፴፱።
፴፫ ሀ አልማ ፪፡፳።
፴፫ ለ አልማ ፴፪፡፩–፪።
ᵃ፰፫ ሀ ᵃ ለ አልማ ፴፯፡፩–፲፪።
ᵐ ቅ.መ.መ. ቅዱስ።
ᵃ ለ አልማ ፴፰፡፩–፪።

አምላካቸውን ትዕዛዛት ለመጠበቅ ጥረት ያደርጉ ነበር።

፲ እናም እንዲህ ሆነ ሞሮኒም ሞተ። የመሣፍንቱ ሰላሳ ስድስተኛ የንግስና ዘመንም እንደዚህ ተፈፀመ።

፲፩ እናም እንዲህ ሆነ በመሣፍንቱ ሰላሳ ሰባተኛ የንግስና ዘመን ብዙ ሰዎች፣ እንዲሁም በአንድነት ወደ አምስት ሺህ አራት መቶ የሚጠጉ፣ ከሚስቶቻቸው እናም ከልጆቻቸው ጋር ከዛራሔምላ ምድር ወጥተው በምድሪቱ [a]በስተሰሜን በኩል ሄዱ።

፲፪ እናም እንዲህ ሆነ ሀጋዝ፣ እጅግ ትጉህ ሰው ስለነበር፣ ስለዚህ ሄደና በወደመው ስፍራ በለጋስ ምድር ዳርቻ እጅግ ታላቅ የሆነ መርከብ ሰራ፤ እናም [b]በቀጭኑ በምድሪቱ በስተሰሜን በሚያመራው መንገድ ወደ ምዕራብ ባህር ላከው።

፲፫ እናም እነሆ፣ በውስጡ የገቡና ብዙ ስንቅ ይዘውም የተጓዙ ብዙ ኔፋውያን፣ እናም ሴቶችና ልጆች ነበሩ፣ ጉዞአቸውንም ወደ ሰሜን አቅጣጫ አደረጉ። እናም ሰላሳ ሰባተኛው ዓመት ተፈፀመ።

፲፬ እናም በሰላሳ ስምንተኛው ዓመት ይህም ሰው ሌላ መርከቦችን ሰራ። እናም ደግሞ የመጀመሪያዋ መርከብ ተመለሰችና፣ ከዚህ የበለጡ ብዙ ሰዎችም ገቡባት፤ እናም እነርሱ ደግሞ ብዙ ስንቅ ያዙና፣ በምድሪቱ በስተሰሜን በኩል በድጋሚ ተላኩ።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ ከዚህ በኋላ ስለእነርሱ ምንም አልተሰማም ነበር። በጥልቅ ባህሩ ውስጥ ሰጥመዋል ብለን ገምተንም ነበር። እናም እንዲህ ሆነ ሌላኛዋ መርከብም ሄደች፤ እርሷም የት እንደደረሰችም አላወቅንም ነበር።

፲፮ እናም እንዲህ ሆነ በዚህ ዓመት በምድሪቱ [c]በስተሰሜን በኩል የሄዱ ብዙ ሰዎች ነበሩ። እናም ሰላሳ ስምንተኛው ዓመት እንደዚህ ተፈፀመ።

፲፯ እናም እንዲህ ሆነ በመሣፍንቱ ሰላሳ ዘጠነኛ የንግስና ዘመን፣ ሺብሎንም ሞተ፣ እናም ወደዚያች ምድር ለሄዱት ሰዎች ስንቅ ለመውሰድ ቆሪያንቶን በምድሪቱ በስተሰሜን በኩል በመርከብ ሄደ።

፲፰ ስለዚህ ሺብሎን ከመሞቱ በፊት ለሔለማን ልጅ፣ በአባቱ ስም [d]ሔለማን ተብሎ ለሚጠራው፣ ቅዱስ የሆኑትን ነገሮች መስጠቱ አስፈላጊ ነበር።

፲፱ እናም እነሆ፣ በሔለማን እጅ የነበሩት [e]የተቀረጹ ጽሑፎች ሁሉ ተፅፈው፣ እናም በአልማ [f]እንዳይሄዱ ከታዘዙት በስተቀር፣ በምድሪቱ ሁሉ በሰው ልጆች መካከል ተልከዋል።

፲፲ ይሁን እንጂ፣ እነዚህ ነገሮች ቅዱስ ሆነው መቀመጥ ይኖርባቸዋል፣ እናም ከትውልድ እስከ ትውልድ [g]መተላለፍ ይኖርባቸዋል፤ ስለዚህ በዚህ ዓመት ሺብሎን ከመሞቱ በፊት እነዚህ ነገሮች ለሔለማን ተሰጡት።

፲፲ እናም እንዲህ ሆነ ደግሞም በዚህ ዓመት ጥቂት ወደ ላማናውያን የሄዱ ተገንጣዮች ነበሩ፤ እናም በኔፋውያን ላይ በድጋሚ ለቁጣ ተነሳስተው ነበር።

፲፳ እናም ደግሞ በዚሁ ዓመት ከሞሮኒሀ ሰዎች ጋር፣ እንዲሁም [h]ከሞሮኒሀ ወታደሮች ጋር ለመዋጋት ከብዙ ወታደሮች ጋር በመሆን መጡ፤ ሆኖም ላማናውያን ተሸነፉና ወደራሳቸው ምድር በድጋሚ ተመልሰው ተባረሩና በብዙ ጥፋትም ተሰቃዩ።

፲፳፩ እናም በኔፊ ህዝብ ላይ የመሣፍንቱ ሰላሳ ዘጠነኛ የንግስና ዘመን እንደዚህ ተፈፀመ።

፲፳፪ እናም የአልማ ታሪክና፣ የልጁ የሔለማን፣ እንዲሁም ደግሞ የልጁ የሺብሎን ታሪክ በዚሁ ተፈፀመ።

---

[a] ሀ አልማ ፳፪፡ ፴፩።
[b] ሀ አልማ ፳፪፡ ፴፪፤ ኤተር ፲፡ ፳።
[c] ሀ ሔለ. ፫፡ ፲፩–፲፪።
[d] ሀ ደግሞም የመፅሐፈ ሔላማን ርዕስን ተመልከቱ።
[e] ሀ አልማ ፲፳፡ ፴፯።
[f] ለ አልማ ፴፯፡ ፳፯–፴፪።
[g] ሀ አልማ ፴፯፡ ፴።
[h] ሀ አልማ ፳፡ ፳፫።

መፅሐፈ ሔለማን

የኔፋውያን ታሪክ። የእነርሱም ጦርነትና ፀብ፣ እናም መለያየታቸው። እናም ደግሞ የሔለ ማን ልጅ በነበረው፣ የሔለማን መዝገብ መሰረት፣ እናም ደግሞ በልጆቹ መዛግብት መሰ ረት፣ ከክርስቶስ መምጣት በፊት እርሱ እስከመጣበት ጊዜ ድረስ የነበረው የብዙ ቅዱ ሳን ነቢያት ትንቢቶች። እናም ደግሞ ብዙ ላማናውያን ተለውጠዋል። የመለወጣቸው ታሪክ። እስከ ክርስቶስ መምጣት ድረስ መፅሐፈ ሔለማን ተብሎ በተጠራው በሔለማንና በልጆቹ መዝገብ መሰረት የላማናውያን ፅድቅና፣ የኔፋውያን ኃጢያት፣ እና እርኩሰት፣ እናም ሌሎች የመሣሰሉ ታሪኮች።

ምዕራፍ ፩

ፓሆራን ሁለተኛው ዋና ገዢ ሆነ፣ እናም በቂሽቁመን ተገደለ—ፓኩሜኒ የፍርድ ወንበሩን ስፍራ ያዘ—ቆሪያንተመር የላ ማናውያን ወታደሮችን መራ፣ ዛራሔም ላን ወሰደና፣ ፓኩሜኒን ገደለ—ሞሮኒያሃ ላማናውያንን አሸነፈና፣ ዛራሔምላን በድ ጋሚ ወሰደ፣ እናም ቆሪያንቱም ተገደለ። ከ፶፪–፶ ም.ዓ. ገደማ።

እናም አሁን እነሆ እንዲህ ሆነ በኔፊ ህዝብ ላይ በመሣፍንቱ አርባኛ ዓመት የንግስ ዘመን፣ በኔፋውያን ህዝቦች መካከል ከባድ ችግር መሆን ጀመረ።

፪ እነሆም "ፓሆራን ሞተ፣ እናም ምድር ሁሉ ወደሚሄዱበት ሄደ፤ ስለዚህ የፓሆ ራን ልጆች ከነሱት መካከል የፍርድ ወን በርን ማን መውሰድ ይገባዋል በሚል ከባድ ፀብ ተጀመረ።

፫ እንግዲህ የፓሆራን ልጆች፣ ለፍርድ ወንበሩ ይጣሉ የነበሩት፣ ደግሞም ህዝቡ እንዲጣላ የሚያደርጉት ስማቸው እነ ዚህ ናቸው፥ ፓሆራን፣ ፓአንኪ፣ እናም ፓኩሜኒ ነበሩ።

፬ እንግዲህ የፓሆራን ወንዶች ልጆች እነ ዚህ ብቻ አይደሉም (ምክንያቱም እርሱ ብዙ ነበሩት)፤ ነገር ግን እነዚህ ለፍርድ ወንበሩ ይጣሉ የነበሩት ናቸው፤ ስለዚህ፣ በህዝቡ መካከል ሶስት ቦታ መከፋፈል እን ዲሆን አደረጉ።

፭ ይሁን እንጂ፣ እንዲህ ሆነ ፓሆራን "በህዝቡ ድምፅ ዋና ዳኛ፣ እናም በኔፊ ህዝብ ላይ ገዢ እንዲሆን ተሾመ።

፮ እናም እንዲህ ሆነ ፓኩሜኒ የፍርድ ወንበሩን ማግኘት እንደማይችል በተመ ለከተ ጊዜ፣ ከህዝቡ ድምፅ ጋር ተባበረ።

፯ ነገር ግን እነሆ፣ ፓአንኪ እናም ከህ ዝቡ መካከል ገዢአቸው እንዲሆን ከፈለ ጉት ሰዎች ጥቂቶች እጅግ ተናደው ነበር፤ ስለዚህ ሰዎቹ በወንድሞቻቸው ላይ እንዲ ያምፁ መሸንገል ሊጀምር ተዘጋጅቶ ነበር።

፰ እናም እንዲህ ሆነ ይኸንን በሚያደር ግበት ወቅት፣ እነሆ ተወስዶ ነበርና፣ እንደ ህዝቡም ድምፅ ክስ ቀርቦበት ነበር፣ እናም ሞት ተፈረደበት፤ ምክንያቱም እርሱ በአ መፅ ተነሳስቶና፣ "የህዝቡን ነፃነት ለማጥ ፋት ተመኝቶ ነበርና።

፱ እንግዲህ ፓአንኪ ገዢአቸው እንዲ ሆን የፈለጉት ሰዎች ሞት እንደተፈረደበት በተመለከቱ ጊዜ፤ ስለዚህ ተናደው ነበር፣ እናም እነሆ፣ ወደ ፓሆራን የፍርድ ወንበ ርም አንድ ቂሽቁመንን ላኩ፣ እናም ፓሆ ራንን በፍርድ ወንበሩ ላይ እንዳለ ገደለው።

፲ እናም የፓሆራን አገልጋዮችም ተከት ለውት ነበር፤ ነገር ግን እነሆ የቂሽቁመን ሽሽቱ ፈጣን በመሆኑ ማንም ሰው ሊደር ስበት አልቻለም።

፲፩ እናም ወደላኩት ሰዎች ዘንድ ሄደ፣ እናም ሁሉም ቃል ኪዳን ገቡ፣ አዎን፣ ቂሽቁመን ፓሆራንን መግደሉን ለማንም ላለመናገር በዘለአለማዊው ፈጣሪያቸው ስም ቃል ኪዳን ገቡ።

፩ ፪ *ሀ* አልማ ፶፣ ፶፯። ፩ *ሀ* ሞዛያ ፳፱፣ ፳፯–፳፱። ፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. መብት።

፲፪ ስለዚህ፣ ቂሽቁመን ፓሆራንን በገደ
ለበት ጊዜ በመደበቁ፣ በኔፊ ህዝብ መካከል
አይታወቅም ነበር። እናም ቂሽቁመንና ከእ
ርሱ ጋር ቃል የገቡት ቡድኖቹ ሁሉ እን
ዳይገኙ በመሆን እራሳቸውን ከህዝቡ ጋር
ቀላቀሉ፤ ነገር ግን የተገኙት በሙሉ ᵐሞት
ተፈረደባቸው።

፲፫ እናም አሁን እነሆ፣ ፓኩሜኒ በወ
ንድሙ ፓሆራን ምትክ ለመንገስ በህዝቡ
ድምፅ ዋና ዳኛና ገዢ እንዲሆን ተሹሞ
ነበር፤ እናም ይህ በመብቱ መሰረት ነበር።
ይህ ሁሉ የተደረገውም በመሣፍንቱ አርባ
ኛው ዓመት የንግስና ዘመን ነበር፤ ይህም
ፍፃሜው ነበር።

፲፬ እናም እንዲህ ሆነ በመሣፍንቱ አርባ
አንደኛ ዓመት የንግስና ዘመን፣ ላማናው
ያን ለመቆጠር የማይችሉ ብዛት ያላቸውን
ወታደሮች በአንድነት ሰበሰቡ፤ እናም በጎ
ራዴም፣ በሻምላም፣ በጦርም፣ በቀስትም፣
እናም በብረት ኮፍያና፣ በደረት ኪስ እን
ዲሁም በሁሉም ዓይነት ጋሻዎች አስታ
ጠቁአቸው።

፲፭ እናም ከኔፋውያን ጋር ለመዋጋት
በድጋሚ መጡ። ቆሪያንተመር ተብሎ
በሚጠራም ሰው ይመሩ ነበር፤ እርሱም
የዛራሔምላ ትውልድ ነበር፤ እናም እርሱ
ከኔፋውያን መካከል የተገነጠለ ነበር፤ እር
ሱም ትልቅና ኃያል ሰው ነበር።

፲፮ ስለዚህ፣ የላማናውያን ንጉስ ስሙም
ቱባሎት ተብሎ የሚጠራ፣ ᵐየአሞሮን ልጅ
የነበረ፣ ቆሪያንተመር ኃያል ሰው በመሆኑ፤
በጉልበቱ፣ እናም ደግሞ በታላቅ ጥበቡ
ኔፋውያንን ለምቋቋም ይችላል፣ እርሱ
ንም በመላክ በኔፋውያን ላይ ኃይልን አገ
ኛለሁ ብሎ ገመተ—

፲፯ ስለዚህ ላማናውያንን በቁጣ እንዲነሳሱ
አደረገና፣ ሠራዊቱን በአንድ ላይ ሰበሰበ፣
እናም ቆሪያንተመርን መሪያቸው እንዲሆን
ሾመው፣ እናም ከኔፋውያን ጋር እንዲዋጉ
ወደ ዛራሔምላ ምድር እንዲዘምቱ አደረገ።

፲፰ እናም እንዲህ ሆነ በመንግስ
ቱም ውስጥ ባለው ፀብና ችግር የተነሳ፣
በዛራሔምላ ምድር በቂ የሆኑ ጠባቂዎችን
አላስቀመጡም ነበር፤ ምክንያቱም ላማና
ውያኖች በምድራቸው መሐል ወደ ታላ
ቋን የዛራሔምላ ከተማ መጥተው ለማጥቃት
አይደፍሩም በማለትም ገምተው ነበርና።

፲፱ ነገር ግን እናም እንዲህ ሆነ ቆሪያንተ
መር ከሰራዊቱ ፊት ዘመተና፣ ወደ ከተማዋ
ነዋሪዎች መጣ፣ እናም ጉዞአቸውም በታ
ላቅ ፍጥነት ስለነበር በዚህም የተነሳ ለኔፋ
ውያን ወታደሮቻቸውን በአንድ ላይ ለመ
ሰብሰብም ጊዜ አልነበራቸውም።

፳ ስለዚህ ቆሪያንተመር በከተማው መግ
ቢያ ላይ የነበሩትን ጠባቂዎች ገደለ፣ እናም
ከመላው ሠራዊቱ ጋር ወደ ከተማው ገቡ፤
እናም ከተማዋን በሙሉ እስከሚወስዱ
ድረስ ተቃዋሚዎቻቸውን በሙሉ ገደሉ
አቸው።

፳፩ እናም እንዲህ ሆነ ዋና ዳኛ የነበረው
ፓኩሜኒ፣ ከቆሪያንተመር ፊት ወደ ከተ
ማዋ ግንብ ሸሸ። እናም እንዲህ ሆነ ቆሪያን
ትመርም ከግንቡ ጋር በማጋጨት መታው፣
በዚህም የተነሳ እርሱ ሞተ። የፓኩሜኒ ቀና
ትም በዚሁ ተፈፀሙ።

፳፪ እናም እንግዲህ ቆሪያንተመር
የዛራሔምላን ከተማ መያዙን በተመለከተ
ጊዜ፣ እናም ኔፋውያን በፊታቸው መሸ
ሻቸውንና፣ መገደላቸውን፣ እናም መወ
ሰዳቸውንና ወደ ወህኒ ቤት መጣላቸውን፣
እንዲሁም በምድሪቱ ሁሉ ጠንካራ ምሽግን
እንደወሰደ በተመለከተ ጊዜ፣ በምድሪቱ
ሁሉ ላይ ይሄድ ዘንድ ልቡ ደፈረ።

፳፫ እናም እንግዲህ በዛራሔምላ ምድር
አልቀረም፤ ነገር ግን ከብዙ ወታደሮቹ ጋር
ወደ ለጋስ ከተማ ተጓዘ፤ ምክንያቱም የም
ድሪቱን ሰሜናዊ ክፍል ያገኝ ዘንድ ወደፊት
መጓዝ እና መንገዱንም በጎራዴ ለማጥራት
የእርሱ ውሣኔ ነበርና።

፳፬ እናም፣ ታላቁ ብርታታቸው በምድ
ሪቱ መካከል መሆኑን ገመተ፤ ስለዚህ በት
ንሽ ቡድኖች ብቻ እንጂ እራሳቸውን በአ

ᵐ ᵐ ቅ.መ.መ. የሞት ቅጣት። ᵐ ᵐ አልማ ፶፪፡ ፫።

ንድነት ለመሰብሰብ ብዙ ጊዜ አልሰጣች
ውም፤ እናም በዚህም ሁኔታ አጠቁአቸ
ውና፣ ወደምድርም ቆርጠው ጣሏቸው።

፳፩ ነገር ግን እነሆ፣ በርካታ ቁጥር ያላ
ቸው ኔፋውያን ቢገደሉም፣ በምድሪቱ
መካከል የነበረው የቆሪያንተመር ጉዞ ለሞ
ሮኒያሃ ትልቅ ጥቅም ሰጠው።

፳፪ እነሆም ሞሮኒያሃ ላማናውያን በምድ
ሪቱ ወደ መሐል ደፍረው እንደማይመጡ፣
ነገር ግን ከዚህ በፊት እንዳደረጉት ከተሞ
ቹን በዳር በኩል ያጠቃሉ በማለት ገምቶ
ነበር፤ ስለዚህ ሞሮኒያሃ ጠንካራ የሆኑ ወታ
ደሮቻቸው በስፍራዎች ዙሪያ የሚገኙትን
እነዚያን ዳርቻዎች እንዲጠብቁ አደረገ።

፳፫ ነገር ግን እነሆ፣ ላማናውያን እንደ
ርሱ ፍላጎት አልፈሩም ነበር፤ ነገር ግን ወደ
ምድሪቱ መሃከል መጡ፣ እናም ዋና ከተማ
የሆነችውን የዛራሔምላን ከተማን ወሰዱ፣
እናም በምድሪቱ ዋና ወደ ሆኑት ቦታዎ
ችም እየሄዱ፣ ወንዶችና፣ ሴቶችንና ልጆ
ችን በመግደል፣ ብዙ ከተሞችንና፣ ብዙ
ጠንካራ ምሽጎችን እየወሰዱ ነበር።

፳፬ ነገር ግን ሞሮኒያሃ ይህንን ባወቀ
ጊዜ፣ ሌሂ ከሠራዊቱ ጋር እነርሱን ወደ
ለጋስ ምድር ከመምጣታቸው በፊት እን
ዲያስቆሙአቸው ወደ ግንባር ላከው።

፳፭ እናም እርሱም እንዲህ አደረገ፤
እናም ወደ ለጋስ ምድር ከመምጣታቸው
በፊት አስቆማቸው፤ ወደ ዛራሔምላም
ምድር ተመልሰው ማፈግፈግ እስኪጀም
ሩም ድረስ ተዋጋቸው።

፳፮ እናም እንዲህ ሆነ ሞሮኒሀ ሲያፈገፍጉ
ጦርነት ገጠማቸው፤ እናም እጅግ አሰቃቂ
ደም መፋሰስ እስከሚሆንም ተዋጉ፤ አዎን፣
ብዙዎች ተገደሉ፤ ከተገደሉትም መካከል
[ሀ]ቆሪያንተመር ይገኝ ነበር።

፳፯ እናም አሁን፣ እነሆ፣ ላማናውያን
በሁሉም አቅጣጫ በኔፋውያን በመከበባቸው
በሰሜን፣ በደቡብ፣ በምስራቅም ሆነ በምዕ
ራብ በኩል ለማፈግፈግ አልተቻላቸውም።

፳፰ እናም ቆሪያንተመር ላማናውያን ኔፋ
ውያን መካከል እንዲገቡ አድርጓል፤ በዚ
ህም የተነሳ በኔፋውያን ኃይል ውስጥ ዋሉ፣
እርሱ ራሱም ተገደለ፣ እናም ላማናውያን
ለኔፋውያን እጃቸውን ሰጡ።

፳፱ እናም እንዲህ ሆነ ሞሮኒያሃ
የዛራሔምላን ከተማ በድጋሚ ወሰደ፤ እናም
እስረኛ ተደርገው የተወሰዱት ላማናውያን
ከምድሪቱ በሰላም እንዲወጡ አደረገ።

፴ እናም የመሣፍንቱ አርባ አንደኛ
ዓመት የንግስና ዘመን በዚሁ ተፈፀመ።

ምዕራፍ ፪

*የሔለማን ልጅ፣ ሔለማን፣ ዋና ዳኛ
ሆነ—ጋድያንቶን የቂሽቁመንን ቡድን
መራ—የሔለማን አገልጋይ ቂሽቁመንን
ገደለው፣ እናም የጋድያንቶን ቡድን ወደ
ምድረበዳው ሸሹ። ከ፣–፣ ም.ዓ. ገደማ።*

፩ እናም እንዲህ ሆነ በመሣፍንቱ አርባ
ሁለተኛ ዓመት የንግስ ዘመን ሞሮኒሀ በድ
ጋሚ በኔፋውያን እና በላማናውያን መካከል
ሰላምን ከመሰረተ በኋላ፣ እነሆ የፍርድ ወን
በሩን ስፍራ የሚይዝ ማንም አልነበረም፤
ስለዚህ በህዝቡ መካከል የፍርድ ወንበሩን
ማን ይያዘው በሚል ፀብ ተጀመረ።

፪ እናም እንዲህ ሆነ የሔለማን ልጅ የነበ
ረው፣ ሔለማን በህዝቡ ድምፅ የፍርድ ወን
በሩን እንዲይዝ ተሾመ።

፫ ነገር ግን እነሆ፣ ፓሆራንን የገደለው
[ሀ]ቂሽቁመን ደግሞም ሔለማንን ለማጥፋት
አደፈጠ፤ እናም ኃጢአቱን ማንም እንዳ
ያውቅበት ወደ ቃልኪዳኑ በገቡት ጓዶቹ
ተደግፎ ነበር።

፬ በብዙ ቃላት እጅግ ባለሙያ የሆነ፣
እናም ደግሞ የግድያንና የዝርፊያን ድብቅ
ስራ ለማከናወን ጥበብ የነበረው አንድ
[ሀ]ጋድያንቶን የተባለ ነበር፤ ስለዚህ እር
ሱም የቂሽቁመን ቡድን መሪ ሆነ።

፭ ስለዚህ በፍርድ ወንበሩ ካስቀመጡት

[ሀ] ሔለ. ፩፡ ፲፭።
[ሀ] ሔለ. ፩፡ ፱።

[ሀ] ቅ.መ.መ. የጋድያንቶን ዘራፊዎች።

በቡድኑ ውስጥ ያሉትን አባላት በህዝቡ መካከል ኃይልና ስልጣን እንደሚሰጣቸ ውእነርሱን፣ እናም ደግሞ ቂሽቁመንንም ሸነገላቸው፣ ስለዚህ ቂሽቁመን ሔለማንን ለማጥፋት ፈለገ።

፲፮ እናም እንዲህ ሆነ ሔለማንን ለማ ጥፋት ወደ ፍርድ ወንበሩ በሚቀርብበት ጊዜ፣ እነሆ አንዱ የሔለማን አገልጋይ በም ሽት ወጥቶ በድብቅ በዚህ ቡድን ሔለማንን ለማጥፋት የተያዘውን ዕቅድ አውቆ እናም ስለአገኘው—

፲፯ እናም እንዲህ ሆነ እርሱም ቂሽቁመንን አገኘውና ምልክት ሰጠው፤ ስለዚህ ሔለማ ንን ይገድለው ዘንድ የፍርድ ወንበሩን እን ዲያሳየው በመፈለግ፣ ቂሽቁመን ዓላማውን ለእርሱ አሳወቃቸው

፲፰ እናም የሔለማን አገልጋይ የቂሽቁመ ንን የልቡን ሀሳብና እንዴት ዓላማው ለግ ድያም እንደሆነ፣ እናም ደግሞ የእርሱ ቡድን አባሎች በሙሉ ለግድያና፣ ለዝር ፊያና ስልጣንን ለማግኘት መሆኑን ባወቀ ጊዜ፣ (እናም ይህ [ሀ]ሚስጥራዊ ዕቅዳቸውና ህብረታቸው በመሆኑ) የሔለማን አገልጋይ ለቂሽቁመን እንዲህ አለው፥ ወደ ፍርድ ወንበሩ እንሂድ።

፲፱ እንግዲህ ይህ ቂሽቁመንን እጅግ አስደ ሰተው፤ ምክንያቱም ያቀደውን እፈፅማለሁ በማለት በመገመቱ ነበር፣ ነገር ግን እነሆ፣ የሔለማን አገልጋይ፣ ወደ ፍርድ ወንበሩ በሚሄዱበት ጊዜ፣ ቂሽቁመንን ልቡ ላይ ወጋው፣ እርሱም ሳያቃስት ወድቆ ሞተ። እናም አገልጋዩ ሮጠና፣ ለሔለማን የተመ ለከተውንና፣ የሰማውን፣ እናም ያደረገውን ነገሮች በሙሉ ነገረው።

፲ እናም እንዲህ ሆነ ሔለማን እነዚ ህን የዘራፊ እናም የስውር ገዳዮች ቡድ ንን በህጉ መሰረት ተይዘው ይገደሉ ዘንድ ሰዎችን ላከ።

፲፩ ነገር ግን እነሆ፣ ጋድያንቶን ቂሽቁመን አለመመለሱን ባወቀ ጊዜ እጠፋለሁ በማ ለት ፈራ፤ ስለዚህ ቡድኖቹ እንዲከተሉት አደረገ። ከምድሪቱ በሚስጢር ወጥተው ወደ ምድረበዳ ሸሹ፤ እናም ከዚህ በኋላ ሔለማን እንዲያመጣቸው ሲላክ ከየትም መገኘት አልቻሉም።

፲፪ እናም ከዚህ በኋላ ስለጋድያንቶን ከዚህ በላይ ይነገራል። እናም በኔፊ ህዝብ ላይ የመሳፍንቱ አገዛዝ አርባ ሁለተኛ ዓመት የንግስና ዘመን ተፈፀመ።

፲፫ እናም እነሆ፣ በዚህ መፅሐፍ መጨረሻ ይህ [ሁ]ጋድያንቶን የመሸነፍ አዎን፣ የኔፋው ያን፣ ፍፁም መጥፋት ምክንያት እንደሆነ ትመለከታላችሁ።

፲፬ እነሆ ይህን በመፅሐፈ ሔለማን መፈ ፀሚያ ውስጥ ነው ማለቴ አይደለም፤ ነገር ግን የፃፍኩትን ታሪክ በሙሉ ከወሰድኩ በት ከኔፊ መፅሐፍ መጨረሻ ማለቴ ነው።

ምዕራፍ ፲

ብዙ ኔፋውያን ወደ ሰሜን ምድር ተጓዙ—የስሚንቶ ቤቶችን ሰሩ፣ እና ብዙ መዛግብ ቶችን አሰቀመጡ—በአስር ሺህዎች የሚ ቆጠሩ ተለወጡ እናም ተጠመቁ—የእ ግዚአብሔር ቃል ሰዎችን ወደ ደህንነት ይመራል—የሔለማን ልጅ ኔፊ የፍርድ ወንበሩን ያዘ። ከ፶፬–፷፬ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንግዲህ እንዲህ ሆነ በመሣፍንቱ አርባ ሶስተኛ ዓመት የንግስ ዘመን በህዝቡ መካከል ጥቂት ልዩነት በፈጠረው ቤተ ክርስቲያን ካለው ጥቂት ኩራት በስተቀር በኔፊ ህዝብ መካከል ፀብ አልነበረም፤ ይህ ጉዳይም በአርባ ሶስተኛው ዓመት መጨ ረሻ ላይ ተስተካከለ።

፪ እናም በአርባ አራተኛው ዓመት በህዝቡ መካከል ፀብ አልነበረም፤ በአርባ አምስተ ኛው ዓመትም ብዙ ፀብ አልነበረም።

፫ እናም እንዲህ ሆነ በአርባ ስድስተ ኛው ዓመት፣ አዎን ብዙ ፀብና መገነጣጠ ሎች ነበሩ፤ ስለሆነም ከዛራሔምላ ምድር

[ሀ] ቅ.መ.መ. የሚስጥር ስብሰባ።

[ሁ] ሔለ. ፮፡፲፤ ፲፮፣ ፪ ኔፊ ፩፡ ፶፪።

የወጡ እጅግ ብዙዎች ነበሩ፤ እናም በምድሪቱ [ሀ]ወደ ሰሜን በኩል ምድሪቱን ለመውረስ ሄዱ።

፬ እናም [ሀ]በታላቁ ውሃ እንዲሁም ወንዝ እስከሚደርሱ ድረስ እጅግ ብዙ ተጓዙ።

፭ አዎን፣ ቀደም ሲል በብዙ ሰዎች ተሰፍሮበት የነበረ በመሆኑም የተነሳ በሁሉም ስፍራ ባዶ ባልሆነው እንዲሁም ምንም ደን በሌለበት የምድሩ ክፍሎች ሁሉ ውስጥ በሙሉ ተበተኑ።

፮ እናም እንግዲህ ከደኑ በስተቀር ባዶ የሆነ ስፍራ በምድሪቱ አልነበረም፤ ነገር ግን ቀደም ሲል ምድሪቱን ወርሰው በነበሩት ሰዎች ታላቅ [ሀ]ጥፋት የተነሳ ምድሪቱ [ለ]የወደመች ተብላ ትጠራ ነበር።

፯ እናም በምድሪቱ ገፅ ትንሽ ዛፍ ብቻ የነበረ በመሆኑ፣ ይሁን እንጂ፣ በምድሪቱ ለመኖር የሄዱ በስሚንቶ ሥራ ባለሙያዎች ሆኑ፤ ስለዚህ የሚኖሩበትንም ቤት ከስሚንቶ ሰርተዋል።

፰ እናም እንዲህ ሆነ ተባዙና፣ ተሰራጩ፣ እንዲሁም ከምድሪቱ ከደቡብ በኩል ወደ ሰሜን ተጓዙ፣ እናም ከባህሩ በስተደቡብ እስከባህሩ በስተ ሰሜን፣ ከባህሩ በስተምዕራብ እስከ [ሀ]ባህሩ በስተምስራቅ ድረስ ምድሪቱን በሙሉ መሸፈን እስከሚጀምሩ ድረስ ተበተኑ።

፱ እናም በምድሪቱ በስተሰሜን በኩል የነበሩት ሰዎች በድንኳንና፣ በስሚንቶ በተሰራው ቤት ውስጥ ኖሩ፣ እናም ከጊዜ በኋላም ቤቶቻቸውን መስሪያ፣ አዎን፣ ከተሞቻቸውንና፣ ቤተመቅደሶቻቸውንና፣ ምኩራቦቻቸውንና፣ ቅዱስ የሆኑ ቦታዎቻቸውንና ሁሉም ዓይነት ህንፃዎቻቸውን መስሪያ እንጨት ይኖራቸው ዘንድ በምድሪቱ ላይ ማንኛውንም ዓይነት ዛፍ እንዲያድግ አደረጉ።

፲ እናም እንዲህ ሆነ በምድሪቱ በስተሰሜን በኩል እጅግ የእንጨት እጥረት ስለነበር፣ ከሌላ ስፍራ ብዙ [ሀ]በመርከብ ያስመጡ ነበር።

፲፩ እና በምድሪቱ በስተሰሜን በኩል ያለው ህዝብ ብዙ ከተሞችን ከእንጨትና ከስሚንቶ ይሰሩ ዘንድ አስቻሏቸው።

፲፪ እናም እንዲህ ሆነ በትውልዳቸው ላማናውያን የነበሩ ብዙ [ሀ]የአሞን ሰዎችም ደግሞ ወደዚህች ምድር ሄዱ።

፲፫ እናም እንግዲህ ስለዚህ ህዝብ ስራ የተቀመጡ፣ በብዙዎቹ በእነዚህ ሰዎች የተለዩ፣ እናም ትልቅ የሆኑ እነርሱን በተመለከተ የሚናገሩ ብዙ መዛግብት ተጠብቀዋል።

፲፬ ነገር ግን እነሆ፣ የዚህ ህዝብ ስራ መቶኛው ክፍል፤ አዎን፣ የላማናውያንና የኔፋውያንና፣ ጦርነታቸውና፣ ፀባቸው፣ እናም ጥላቸውና፣ ሰበካቸውም፣ ትንቢታቸውም፣ የመርከብ ጉዞአቸውና፣ የመርከብ አሰራራቸውንና፣ [ሀ]የቤተመቅደስ አሰራራቸውንና፣ የምኩራቡንና፣ የቅዱሳን ስፍራዎቻቸውንና፣ ፅድቃቸውንና፣ ኃጢአታቸውንና፣ የግድያቸውና፣ ስርቆታቸው፣ እናም የዝርፊያቸው፣ እንዲሁም የሁሉም ዓይነት እርኩሰትና ዝሙት ታሪክ በዚህ ስራ ውስጥ ሊጠቃለሉ አይችሉም።

፲፭ ነገር ግን እነሆ፣ ብዙ መጻሕፍትና ከሁሉም ዓይነት ብዙ መዛግብት አሉ፣ እናም በኔፋውያን በተለይ ተጠብቀዋል።

፲፮ እናም ኔፋውያን በመተላለፍ እስከሚወድቁና እስከሚገደሉ፣ እስከሚዘረፉና፣ እስከሚታደኑና፣ እስከሚባረሩ፣ እናም እስከሚታረዱና፣ በምድር ገፅ ላይ እስከሚበተኑ፣ እንዲሁም [ሀ]ኔፋውያን ተብለው መጠራት እስከሚያቆሙ ድረስ ከላማናውያን ጋር እስከሚቀላቀሉ፣ እነርሱ ኃጢአተኞችና፣ አረመኔዎች፣ እናም ኃይለኞች እስከሚሆኑ፣ አዎን፣ ላማናውያንም እንኳን እስከሚሆኑ ድረስ ከአንዱ ትውልድ ወደ ሌላኛው በኔፋውያን [ለ]ተላልፈዋል።

፫ ፫ ሀ አልማ ፷፫፥፬።
፬ ሀ ሞዛያ ፰፥፰፤ ሞር. ፮፥፬።
፮ ሀ ሞዛያ ፳፩፥፳፭–፳፯።
ለ አልማ ፳፪፥፴፩።
፰ ሀ አልማ ፳፪፥፳፯፤ ፴፪።
፲ ሀ አልማ ፷፫፥፭–፰።
፲፪ ሀ አልማ ፳፯፥፳፩–፳፮።
፲፬ ሀ ፪ ኔፊ ፭፥፲፮፤ ያዕቆ. ፩፥፲፯፤ ፫ ኔፊ ፲፩፥፩።
፲፮ ሀ አልማ ፵፭፥፲፪–፲፬።
ለ ፩ ኔፊ ፭፥፲፮–፲፱፤ አልማ ፴፯፥፬።

፲፯ እናም አሁን እኔም በድጋሚ ወደራሴ ታሪክ እመለሳለሁ፤ ስለዚህ የተናገርኳቸው የሆኑት ታላቁ ፀብና፣ ረብሻና፣ ጦርነት፣ እናም ጥል፣ በኔፋውያን መካከል ከተፈ ፀመ በኋላ ነበር።

፲፰ አርባ ስድስተኛው የመሣፍንቱ የንግስ ዘመንም ተፈፀመ፤

፲፱ እናም እንዲህ ሆነ በምድሪቱ አሁንም ታላቅ ፀብ ነበር፤ አዎን፣ እንዲሁም በአርባ ሰባተኛው ዓመትም፣ እናም ደግሞ በአርባ ስምንተኛውም ዓመት።

፳ ይሁን እንጂ ሔለማን በፅድቅና በእኩ ልነት የፍርድ ወንበሩን ያዘ፤ አዎን የእግዚ አብሔርን ስርዓትና፣ ህግጋት፣ እናም ትዕ ዛዛት ለመጠበቅ ጥረት አደረገ፤ እናም በእ ግዚአብሔር ፊት ትክክል የሆነውን ያለማ ቋረጥ ያደርግ ነበር፤ በምድሪቱም ላይ እስ ከሚበለፅግ ድረስ እንደ አባቱ ኖሯል።

፳፩ እናም እንዲህ ሆነ እርሱ ሁለት ወንድ ልጆች ነበሩት። ለታላቅየው [a]የኔፊን ስምና፣ ለታናሽየው [b]የሌሂን ስም ሰጣቸው። እናም በጌታ ማደግ ጀመሩ።

፳፪ እናም እንዲህ ሆነ በመሣፍንቱ በኔፊ ህዝብ ላይ በአርባ ስምንተኛው ዓመት የን ግሥ ዘመን ማብቂያ ገደማ በኔፋውያን መካ ከል ጦርነቱ፣ እናም ፀቡ በመጠኑ መቆም ጀመረ።

፳፫ እናም እንዲህ ሆነ በመሣፍንቱ አርባ ዘጠነኛ ዓመት የንግስና ዘመን፣ እነርሱም በዚያን ጊዜም ቢሆን በመንግስት ከበላይ በነበሩት ከማይታወቁት፣ ሁሉም በተረጋ ጋው ስፍራ ቀማኛው [c]ጋድያንቶን ካደራ ጀው የሚስጥር ሴራዎች በስተቀር በምድ ሪቱም የማያቋርጥ ሰላም ተመሰረተ፤ ስለ ዚህ ከምድሪቱም ፈፅሞ አልጠፉም ነበር።

፳፬ እናም እንዲህ ሆነ በዚሁ ዓመት በቤ ተክርስቲያኗ እጅግ ታላቅ ብልፅግና ሆነ፤ በሺዎች የሚቆጠሩትም ወደ ቤተክርስቲ ያኗ መጡ፣ እናም ንስሃ በመግባት ተጠ መቁ።

፳፭ እናም የቤተክርስቲያኗ ብልፅግናም ታላቅ ሆኖ፣ እናም በጣም ብዙ በረከት በህዝቡ ላይ ስለወረደ፤ ታላላቅ ካህናትና፣ መምህራንም እራሳቸው ከልክ በላይ ተገ ርመው ነበር።

፳፮ እናም እንዲህ ሆነ የጌታ ስራ ብዙ ነፍ ሳትን፣ አዎን አስር ሺዎችን ያህል፣ በማ ጥመቅ፣ እናም ወደ እግዚአብሔር ቤተክ ርስቲያኗ በማምጣት በለጸገ።

፳፯ ስለዚህ ጌታ ከልብ በመሆን ቅዱስ ስሙን ለሚጠሩ ሁሉ እርሱ መሀሪ እንደ ሚሆን እንደዚህ እንመለከታለን።

፳፰ አዎን፣ የእግዚአብሔር ልጅ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ለሚያምኑ፣ [d]የሰ ማይ በር [e]ለሁሉም ክፍት እንደሆነም እን ደዚህ እንመለከታለን።

፳፱ አዎን፣ ማንም ቢሆን [f]ህያው የሆ ነውንና ኃያል የሆነውን፣ የዲያብሎስን ዕቅድ፣ ብልጠትና ወጥመድ የሚበታት ነውን፣ እናም የክርስቶስ የሆኑትን ሰዎች በቀጭኑና [g]ጠባብ በሆነው ጎዳና፣ ኃጢአ ተኞችንም ሊውጣቸው ከተዘጋጀው ከዘለዓ ለማዊው ሓጉስቁልና ባሻገር የሚመራቸውን [h]የእግዚአብሔርን ቃል አጥብቆ የያዘ—

፴ ነፍሳቸውም፣ አዎን የማይሞተው ነፍሳቸው በመንግስተ ሰማያት በእግዚአ ብሔር [i]ቀኝ እጅ፣ ከአብርሃምና፣ ከይስ ሀቅ፣ እናም ከያዕቆብና፣ ከቅዱሳን አባቶቻ ችን ጋር ለማስቀመጥ፣ ከእንግዲህም ወደ ውጭ አይሄዱ ዘንድ እንደሚያደርግ እን መለከታለን።

፴፩ እናም በዚህ ዓመት በዛራሔምላ ምድር፣ እናም በዙሪያው ሁሉ፤ በኔፋው ያን በተያዙት ቦታዎች እንኳን ሁሉ የማያ ቋርጥ ደስታ ነበር።

፴፪ እናም እንዲህ ሆነ በአርባ ዘጠነኛው

፳፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. ኔፊ፣ የሔለማን ልጅ።
ለ ቅ.መ.መ. ሌሂ፣ የኔፋውያን ሚስዮን።
፳፫ *ሀ* ሔለ. ፪ ፡ ፩።
፳፭ *ሀ* ፪ ኔፊ ፴፩ ፡ ፱፣ ፲፯።
ለ የሐዋ. ፲ ፡ ፳፰፤ ሮሜ ፪ ፡ ፲–፲፩።
፳፱ *ሀ* ዕብ. ፬ ፡ ፲፪፤ ት. እና ቃ. ፲፩ ፡ ፪።
ለ ፪ ኔፊ ፱ ፡ ፴፩፤ ፴፫ ፡ ፱።
ሐ ፩ ኔፊ ፲፭ ፡ ፳፰–፴።
መ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ቃል።
፴ *ሀ* ማቴ. ፳፭ ፡ ፴፫–፴፬።

ዓመት ሰላምና እጅግ ታላቅ ደስታ ነበር፤ አዎን፣ እናም ደግሞ በመሣፍንቱም ሀምሳኛ ዓመት የንግስ ዘመን የማያቋርጥ ሰላምና ታላቅ ደስታ ነበር።

፴፲ እናም በቤተክርስቲያኗ—ወደ እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ሳይሆን፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ተብለው እራሳቸውን ከሚጠሩት ሰዎች ልብ ውስጥ—መግባት ከጀመረው ኩራት በስተቀር በመሣፍንቱ ሀምሳ አምስተኛ ዓመት የንግስ ዘመንም ሰላም ነበር

፴፲፩ እናም ብዙዎች ወንድሞቻቸውን እስከሚያሳድዱአቸው ድረስ [ሀ]በኩራት ተወጠሩ። አሁን ይህ ታላቅ ክፋት ትሁት የሆኑትን ሰዎች ይበልጥ ለታላቅ ስደት እናም ስቃይ እንዲገፉ የሚያደርግ የነበረው።

፴፲፪ ይሁን እንጂ ዘወትር [ለ]ያሙ፣ እንዲሁም [ሐ]ፀለዩ፣ እናም ነፍሳቸውን በደስታና በመፅናናት እስከሚሞሉ ድረስም፣ አዎን፣ ልቦቻቸውን ለእግዚአብሔር በፍቃድ [መ]በመስጠት በሚመጣው [ሠ]ቅድስና ልቦቻቸው [ረ]እንዲጸዱና እንዲቀደሱ እስከሚያደርጉ ድረስ [ሰ]በትህትና እየጠነከሩ፣ እናም በክርስቶስ እምነታቸውን እየጸኑ ሄዱ።

፴፲፫ እናም እንዲህ ሆነ በህዝቡ ልብ ውስጥ ከገባው ታላቅ ኩራት በቀር ሀምሳ ሁለተኛው ዓመትም በሰላም ደግሞ ተፈፀመ፤ እናም የዚህ መንስኤ በምድሪቱ ከነበራቸው እጅግ ታላቅ [ሀ]ሀብትና ብልፅግና ነበር፤ ይህም በእነርሱ ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ ሄደ።

፴፲፬ እናም እንዲህ ሆነ በመሣፍንቱ ሀምሳ ሶስተኛ ዓመት የንግስ ዘመን ሔለማን ሞተ፤ ታላቁ ልጁ ኔፊም በእርሱ ምትክ መንገስ ጀመረ። እናም እንዲህ ሆነ የፍርድ ወንበሩንም በጽድቅና በእኩልነት ያዘው፤ አዎን የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ጠበቀና፣ በአባቱ መንገድ ተራመደ።

ምዕራፍ ፴

ከኔፋውያን የተገነጠሉትና ላማናውያን ኃይላቸውን አቀላቀሉ፣ እናም የዛራሔምላ ምድርን ያዙ—የኔፋውያን ሽንፈት የመጣው በኃጢአታቸው ምክንያት ነው—ቤተክርስቲያኗ ተመናመነች፣ እናም ህዝቡ እንደላማናውያን ደካማ ሆነ። ከ፴፲–፴ ም.ዓ. ገደማ።

፴ እናም እንዲህ ሆነ በሀምሳ አራተኛው ዓመት በቤተክርስቲያኗ ብዙ መለያየት ነበር፤ እናም ደግሞ ብዙ ደም እስከሚፈስ ድረስ በህዝቡ መካከልም [ሀ]ፀብ ነበር።

፴፩ እናም አማፅያን የሆኑት ተገደሉና፣ ከምድሪቱ ተባረሩ፣ እናም ወደ ላማናውያን ንጉስ ሄዱ።

፴፪ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያንን ከኔፋውያን ጋር በውጊያ ለማወክ ጥረት አደረጉ፤ ነገር ግን እነሆ ላማናውያን የእነዚያን የተገነጠሉትን ቃል ለመስማት እስከማይፈልጉም እጅግ ፈርተው ነበር።

፴፫ ነገር ግን እንዲህ ሆነ በመሣፍንቱ ሀምሳ ስድስተኛው ዓመት የንግስና ዘመን ከኔፋውያን ወደላማናውያን የሄዱ [ሀ]ተቃዋሚዎች ነበሩ፤ እናም በኔፋውያን ላይ ለቁጣ በማነሳሳት ድልን አገኙ፤ እናም ሁሉም በዚያን ዓመት በሙሉ ለጦርነት ተዘጋጅተው ነበር።

፴፬ እናም በሀምሳ ሰባተኛው ዓመት ለውጊያ በኔፋውያን ላይ መጡና፣ የሞትን ስራ ጀመሩ፤ አዎን በመሣፍንቱ ሀምሳ ስምንተኛ ዓመት የንግስ ዘመን የዛራሔምላን ምድር አዎን እናም ደግሞ ከለጋስ ምድር አጠገብ ያሉትን ቦታዎች በሙሉ ለመያዝ ድል አገኙ።

፴፩ ሀ ቅ.መ.መ. ኩራት።
፴፪ ሀ ቅ.መ.መ. ጸም፣ መጾም።
ለ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
ሐ ፪ ዜና ፴፡፳፤
ሞዛያ ፲፡፲፱።
መ ቅ.መ.መ. ቅድስና።
ሠ ቅ.መ.መ. ንጹህ፣ ንጹህነት።
ረ ቅ.መ.መ. ትሁት፣ ትሕትና።
፴፫ ሀ ቅ.መ.መ. ሀብቶች።
፴ ፴ ሀ ፲ ኔፊ ፲፰፡፳፱።
፴ ሀ ሔለ. ፭፡፲፯።

፮ እናም ኔፋውያንና የሞሮኒሀም ወታደ
ሮች ወደ ለጋስ ምድር ተባረሩ፤
፯ እናም ከባህሩ በስተምዕራብ በኩል
እስከምስራቅ ከላማናውያን እራሳቸውን
ሸሸጉ፤ ኔፋውያን ሰሜናዊውን ሀገራቸውን
ለመከላከል ወታደሮቻቸውን የሸሸጉበት፣
እና ያሰፈሩበት መስመር የአንድ ቀን ጉዞ
ያህል ነበር።
፰ እናም እነዚያ ከኔፋውያን የተገነጠሉት
ከብዙ ላማናውያን ወታደሮች እርዳታ ጋር
በምድሪቱ በደቡብ በኩል ያሉትን የኔፋው
ያንን ይዞታዎች በሙሉ አገኙ። እናም ይህ
ሁሉ የሆነው በመሣፍንቱ ሀምሳ ስምንተ
ኛና ዘጠነኛ የንግስ ዘመን ነበር።
፱ እናም እንዲህ ሆነ በመሣፍንቱ ስልሳኛ
ዓመት የንግስ ዘመን ሞሮኒሀ ከሠራዊቱ ጋር
የምድሪቱን ብዙ ቦታዎች ለማግኘት ተሳካ
ለት፤ አዎን እነርሱም በላማናውያን እጅ
የወደቁትን ብዙ ከተሞች በድጋሚ አገኙ።
፲ እናም እንዲህ ሆነ በመሣፍንቱ ስልሳ
አንደኛ የንግስና ዘመን የይዞታዎቻቸውን
ግማሽ እንኳን በድጋሚ ለማግኘት ተሳካ
ላቸው።
፲፩ እንግዲህ ይህ የኔፋውያን ታላቅ
ጥፋት፣ እናም በመካከላቸው የነበረው
ታላቅ ሞት፣ በመካከላቸው በነበረው በኃ
ጢአተኝነታቸውና በእነርሱ ርኩስና ባይሆኑ
ኖሮ አይኖርም ነበር፤ አዎን፣ እናም ይህ
ደግሞ የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን አባል
ነን በሚሉትም መካከል የሚገኝም ነበር።
፲፪ እናም ይህም [a]በልባቸው ኩራት፣
እጅግ [b]ሀብታም በመሆናቸው የተነሳ፣
አዎን [c]ድሆችን በመጨቆናቸው፣ ለረሃብ
ተኞችም ምግባቸውን ስለከለከሉአቸው፣
ከታረዙት የሚለብሱትን በመከልከላቸው፣
ትሁት የሆኑ ወንድሞቻቸውንም በጥፊ ስለ
መቱአቸው፣ ቅዱስ በሆነውም ስለተሳለቁ፣
የትንቢትን እና የራዕይን መንፈስ በመካ
ዳቸው፣ በመግደላቸው፣ በመዝረፋቸው፣
በመዋሸታቸው፣ በመስረቃቸው፣ ዝሙ
ትን በመፈፀማቸው፣ ለፀብ በመነሳሳታ
ቸው፣ እናም ወደኔፊ ምድር፣ ከላማናው
ያን መካከል፣ ጥለው በመሄዳቸው ምክን
ያት ነበር—
፲፫ እናም በዚህ በታላቁ ኃጢአታቸው
የተነሳና፣ በጉልበታቸውም [d]በመኩራታ
ቸው፣ በእራሳቸው ጥንካሬ ተትተው ነበር፤
ስለዚህ አልበለፀጉም፣ ነገር ግን ተሰቃዩና፣
ተመቱ፣ እናም ምድሪቱን በሙሉ ለማጣት
እስከሚቀርቡ ድረስ ከላማናውያን ፊት
ተባርረዋል።
፲፬ ነገር ግን እነሆ፣ ሞሮኒሀ በክፋታቸው
የተነሳ ለህዝቡ ብዙ ነገሮችን ሰበከላቸው፣
እናም ደግሞ የሔለማን ልጆች የነበሩት
[e]ኔፊና ሌሂ፣ ለህዝቡ ብዙ ነገሮችን ሰበኩ፣
አዎን እናም ስለክፋታቸውና፣ ለኃጢአታ
ቸው ንስሃ ካልገቡ በእነርሱ ላይ ምን እንደ
ሚመጣም ተነበዩላቸው።
፲፭ እናም እንዲህ ሆነ ንስሃ ገቡ፤ እናም
ንስሃ በመግባታቸውም መበልፀግ ጀመሩ።
፲፮ ሞሮኒሀ ንስሃ መግባታቸውን በተመ
ለከተ ጊዜ፣ የንብረቶቻቸውን ግማሽ እናም
የምድራቸውን ግማሽ እስከሚያገኙ ድረስ
እነርሱን ከቦታ ቦታ፣ እንዲሁም ከከተማ
ከተማ ለመምራት ሞከረ።
፲፯ እናም የመሣፍንቱ ሥልሳ አንደኛ የን
ግስና ዘመን እንደዚህ ተፈፀመ።
፲፰ እናም እንዲህ ሆነ በመሣፍንቱ ስልሳ
ሁለተኛ የንግስና ዘመን ሞሮኒሀ ከላማና
ውያን ይበልጥ ይዞታዎችን ማግኘት አል
ቻለም።
፲፱ ስለዚህ የተቀረውን ምድር የማግኘት
ዕቅዳቸውን ተዉት፤ ምክንያቱም ላማናው
ያን እጅግ ብዙ ስለ ነበሩ ለኔፋውያን በእ
ነርሱ ላይ ይበልጥ ኃይልን ለማግኘት አስ
ቸጋሪ ሆነ፤ ስለዚህ ሞሮኒሀ የወሰዳቸውን
ቦታዎች ለማቆየት ወታደሮቹን በሙሉ አሰ
ማራ።

፲፪ [a] ሀ አብድ. ፩፡ ፫–፬፤ ት. እና ቃ. ፲፩፡ ፸፪።
[b] ለ ፩ ጢሞ. ፮፡ ፲፯፤
[c] ፪ ኔፊ ፱፡ ፸፪።
[d] ሐ ት. እና ቃ. ፸፪፡ ፸–፸፩።
[e] ፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. ኩራት።
[f] ፲፬ ሀ ሔሉ. ፫፡ ፳፩።

፳ እናም እንዲህ ሆነ የላማናውያን ቁጥር ብዙ በመሆኑ፣ ላማናውያን እንዳያሸንፏ ቸው፣ እናም እንዳይረግጧቸውና፣ እንዳ ይገድሏቸው፣ እንዲሁም እንዳያጠፏቸው ዘንድ ኔፋውያን በጣም ፈርተው ነበር።

፳፩ አዎን የአልማን ትንቢቶች፣ እናም ደግሞ የሞዛያን ቃላት ማስታወስ ጀመሩ፤ እናም አንገተ ደንዳና ህዝቦች መሆናቸው ንና፣ የእግዚአብሔርንም ትዕዛዛት ከንቱ እንዳደረጉ ተመለከቱ፤

፳፪ እናም የሞዛያን፣ ወይም ጌታ ለህዝቡ እንዲሰጥ ያዘዘውን፣ [ሀ]ህግ እንደለወጡትና በእግራቸው እንደረገጡት፣ እናም ህግጋ ቶቻቸው እንደተበላሹና፣ እነርሱም እንደ ላማናውያን አይነት ኃጢአተኞች እስኪሆኑ ድረስ ጎጥያተኛ ህዝቦች እንደሆኑ ተመለ ከቱ።

፳፫ እናም በክፋታቸው የተነሳ ቤተክርስ ቲያኗ [ሀ]መመንመን ጀመረች፤ እናም በት ንቢት መንፈስና፣ በራዕይ መንፈስ እምነት ማጣት ጀመሩ፤ የእግዚአብሔር ፍርድም በእነርሱ ላይ በአትኩሮት ተመለከታቸው።

፳፬ እናም እንደ ወንድሞቻቸው እንደ ላማናውያን [ሀ]ደካማ መሆናቸውን፣ እናም የጌታ መንፈስም ከዚህ በኋላ እንዳላዳናቸ ውም ተመለከቱ፤ አዎን፣ [ለ]የጌታ መንፈስ [ሐ]ቅዱስ ባልሆነ ቤተመቅደስ ስለማይኖርም ከእነርሱ ሸሸ—

፳፭ ስለዚህ ጌታ በአስደናቂውና፣ ወደር በሌለው ኃይል እነርሱን መጠበቁን አቆመ፤ ምክንያቱም [ሀ]እምነት ወደማጣትና፣ በአሰ ቃቂ ኃጢያት ወድቀዋልና፤ እናም ላማና ውያን ከእነርሱ ይልቅ እጅግ ብዙ መሆና ቸውን፣ እናም ወደጌታ አምላካቸው [ለ]በታ ማኝነት ካልጸኑ በማይቀር ሁኔታ መጥፋት እንዳለባቸው ተመለከቱ።

፳፮ እነሆም የላማናውያን ጥንካሬ እንደ እነርሱ ጥንካሬ፣ እንዲሁም አንድ ሰው ለአንድ ሰው አይነት፣ መሆኑን ተመለ ከቱ። እናም ስለዚህ ወደዚህ ታላቅ መተ ላለፍ እንደዚህ ወደቁ፤ አዎን፣ [ሀ]በጥቂት ዓመታት በመተላለፋቸውም ምክንያት እን ደዚህ ደካሞች ሆኑ።

ምዕራፍ ፮

ኔፊ፣ እና ሌሂ እራሳቸውን ለስብከት ሰጡ—ስሞቻቸው እንደቅድመ አያቶ ቻቸው ህይወታቸውን ይመስሉበት ዘንድ ይጋብዛቸዋል—ክርስቶስ ንስሃ የሚገ ቡትን ያድናል—ኔፊና ሌሂ ብዙዎችን ለወጡ፣ እናም ወደ ወህኒ ተወሰዱ፣ እና እሳት እነርሱን ከበባቸው—የጨለማው ጭጋ ግም ሶስት መቶ ሰዎችን ሸፈነ—መሬት ተንቀጠቀጠች፣ እናም ድምፅም ሰዎችን ንስሃ እንዲገቡ አዘዘ—ኔፊና ሌሂ ከመላ ዕክት ጋር ተነጋገሩ፣ እና ብዙ ህዝብም በእሳት ተከበበ። በ[ሀ] ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ በዚሁ ዓመት፣ እነሆ፣ [ሀ]ኔፊ ሴዞራም ተብሎ ለሚጠራ ሰው የፍርድ ወንበሩን ሰጠ።

፪ ህግጋቶቻቸው፣ እናም መንግስታቸው [ሀ]በህዝቡ ድምፅ በመቋቋሙ፣ እናም መልካ ምን [ለ]ከመረጡት ክፉውን የመረጡት ቁጥር ብዙ በመሆኑ ለጥፋት በስለዋል፣ ምክንያ ቱም ህጎቹ ተበላሽተዋልና።

፫ አዎን እናም ይህ ብቻም አልነበረም፤ ለጥፋታቸው ካልሆነ በቀር በህግም ሆነ በፍ ትህ መገዛት እስከማይችሉ ድረስ አንገተ ደንዳናዎች ነበሩ።

፬ እናም እንዲህ ሆነ ኔፊ በክፋታቸውም የተነሳ ታከተው፤ እናም የፍርድ ወንበ ሩን [ሀ]ለቀቀና፣ በቀሩት ቀኖቹ፣ እንዲሁም ደግሞ ወንድሙ ሌሂ በቀሩት ቀኖቹ፣ የእ ግዚአብሔርን ቃል ለማስተማር ኃላፊነትን ወሰዱ፤

፳፪ ሀ አልማ ፩፡ ፩።
፳፫ ሀ ቅ.መ.መ. ክህደት።
፳፬ ሀ ሞዛያ ፩፡ ፲፫።
ለ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
ሐ ሞዛያ ፪፡ ፴፯፤
አልማ ፯፡ ፳፩፣ ፴፬፡ ፴፯።
፳፭ ሀ ቅ.መ.መ. አለማመን።
ለ ያዕቆ. ፯፡ ፭።
፳፯ ሀ አልማ ፵፯፡ ፰፤
ሔለ. ፲፪፡ ፫–፬።
፳፰ ፩ ሀ ሔለ. ፫፡ ፴፯።
፪ ሀ ሞዛያ ፳፱፡ ፳፭–፳፯።
ለ አልማ ፲፡ ፲፱።
፬ ሀ አልማ ፪፡ ፲፭–፳።

፮ አባታቸው ሔለማን የተናገረውን ቃላት አስታውሰዋልና። እናም እርሱ የተናገራ ቸው ቃላት እነዚህ ናቸው፡

፯ እነሆ፣ ልጆቼ፣ የእግዚአብሔርን ትዕ ዛዛት ለመጠበቅ እንድታስታውሱት እፈ ልጋለሁ፣ እነዚህንም ቃላት ለህዝቡ እን ድታውጁ እፈልጋለሁ። እነሆ ከኢየሩሳ ሌም ምድር ለቀው የወጡትን የመጀመ ሪያ ᵐወላጆቻችንን ስም ሰጥቻችኋለሁ፤ ይህንን ያደረግሁትም ስማችሁን ስታስቡ እነርሱን ታስታውሱ ዘንድ ነው፤ እናም እነርሱን ስታስታውሱ ስራቸውን ታስታ ውሱ ዘንድ ነው፣ ስራቸውንም ስታስታ ውሱ ᵃመልካም እንደነበሩ እንዴት እንደ ተባለና፣ ደግሞ እንደተፃፈ እንድታውቁ ዘንድ ነው።

፰ ስለዚህ፣ ልጆቼ፣ እንደ እነርሱ እንደተ ባለው እናም እንደተጻፈው ስለእናንተ እን ዲባልና ደግሞ እንዲጻፍ መልካም የሆኑትን እንድታደርጉ እፈልጋለሁ።

፱ እናም እንግዲህ ልጆቼ፣ እነሆ ከዚህ የበለጠ እንድታደርጉ የምፈልገው አለኝ፣ ይህ ፍላጎቴም ለመኩራት ብላችሁ እነዚህን ነገሮች አታድርጉ፤ ነገር ግን በሰማይ ለራ ሳችሁ፣ አዎን ዘለዓለማዊ የሆነ እናም የማ ይጠፋን ᵐየሰማይ ሀብትን ታከማቹ ዘንድ፤ አዎን ለአባቶቻችን ይሰጣሉ ብለን ላለመ ገመት ምክንያት እንደሌለን አይነት የዘ ለዓለም ህይወት ᵃየተከበረ ስጦታ ይኖራ ችሁ ዘንድ ይሁን እነዚህን ነገሮች አድርጉ።

፲ አቤቱ ልጆቼ አስታውሱ፣ ንጉስ ቢን ያም ለህዝቡ የተናገረውን ᵐቃላት አስታ ውሱ፣ አዎን፣ በሚመጣው ᵃበአዳኙ የኢየ ሱስ ክርስቶስ ደም ካልሆነ በቀር የሰው ልጅ ሊድንበት የሚችልበት መንገድም ሆነ ዘዴ የለም፤ አዎን፣ ᵃዓለምን ᵐለማዳን እንደ ሚመጣም አስታውሱ።

፲፩ እናም ደግሞ አሙሌቅ በአሞኒህ ከተማ ለዚኤዝሮም የተናገራቸውን ᵐቃላት አስ ታውሱ፤ ምክንያቱም እርሱ ጌታ በእር ግጥ ህዝቡን ለማዳን እንደሚመጣ ተናግ ሯልና፤ ነገር ግን ከኃጢአታቸው ሊያድ ናቸው እንጂ፣ ከነኃጢአታቸው ሊፈውሳ ቸው አይመጣም።

፲፪ እናም ጌታ በንስሃ የተነሳ ከኃጢአታ ቸው እንዲያድናቸው ከአብ ስልጣን ተሰጥ ቶታል፤ ስለዚህ ህዝቡን ወደማዳን ስልጣን እንዲሁም ወደነፍሳቸው ደህንነት የሚያመ ጣቸውን የንስሃን የምስራች ሁኔታ ለመና ገር መላዕክቱን ᵐልኳል።

፲፫ እናም አሁን ልጆቼ አስታውሱ፣ አስ ታውሱ፣ አዳኝ በሆነው የእግዚአብሔር ልጅ በሆነው በክርስቶስ ᵐዓለት ᵃመሰረታ ችሁን መገንባት እንዳለባችሁ፤ ዲያብሎስ ኃይሉን ንፋሱን፣ አዎን፣ ᵃበአውሎ ነፋስ እንደሚወረወር ዘንጉን በላከ ጊዜ፣ አዎን በረዶው፣ እናም ኃይለኛው ውሽንፍር በሚ መታችሁ ጊዜ፣ እርግጠኛ መሰረት በሆነው ሰዎች ከገነቡበት ሊወድቁበት በማይችሉ በት አለት ላይ ስለገነባችሁ እናንተን ወደ ስቃይና ወደባህር ስላጤና መጨረሻ ወደ ሌለው ዋይታ ጎትቶ ለመጣል ኃይል አይ ኖረውም።

፲፬ እናም እንዲህ ሆነ እነዚህ ቃላትን ነበር ሔለማን ለልጆቹ ᵐያስተማራቸው፤ አዎን፣ ብዙ ያልተፃፉ ነገሮችንም እናም ደግሞ ብዙ የተፃፉ ነገሮችንም አስተምሯቸዋል።

፲፭ እናም ቃላቱን አስታውሰዋል፤ እናም ስለዚህ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት በመጠ በቅ ከለጋስ ከተማ በመጀመር በኔፊ ህዝብ

፯ ᵐ ፩ ኔፊ ፩፡ ፩፣ ፫።
ᵃ ፪ ኔፊ ፴፫።
፰ ᵐ ፫ ኔፊ ፲፫፡ ፲፱–፳፩።
ᵃ ት. እና ቃ. ፲፡ ፯።
፱ ᵐ ሞዛያ ፪፡ ፱።
ᵃ ሞዛያ ፫፡ ፲፯–፲፰።
ቅ.መ.መ. የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ።
ሐ ቅ.መ.መ. አለም—ትእዛዛትን የማያከብሩ ሰዎች።
መ ቅ.መ.መ. ቤዛ፣ ማዳን፣ ቤዛነት።
፲ ᵐ አልማ ፲፩፡ ፴፱።
፲፩ ᵐ አልማ ፲፫፡ ፳፱–፳፭።
፲፪ ᵐ ማቴ. ፯፡ ፳፱–፳፯፤ ት. እና ቃ. ፯፡ ፴፱፤ ሙሴ ፯፡ ፱፫።
ቅ.መ.መ. አለት፣ የማዕዘን ድንጋይ።
ᵃ ኢሳ. ፳፰፡ ፲፯፤ ያዕቆ. ፪፡ ፲፯።
ሐ ፫ ኔፊ ፲፡ ፲፭፣ ፳፯።
፲፫ ᵐ ሞዛያ ፩፡ ፩።

ሁሉ መካከል የእግዚአብሔርን ቃል ለማ
ስተማር ተጓዙ።
፲፭ እናም ከዚያን በኋላ ወደ ጊድ ከተ
ማና፣ ከጊድ ከተማ ወደ ሙሌቅ ከተማ
ሄዱ፤
፲፮ እናም በምድሪቱ በስተደቡብ በኩል
ከነበሩት ከኔፊ ሰዎች ጋር እስከሚጓዙ ድረስ
ከአንዱ ከተማ ወደ ሌላኛው ሄዱ፤ እናም
ከዚያ ከላማናውያን መካከል ወደ ዛራሔምላ
ምድር ተጓዙ።
፲፯ እናም እንዲህ ሆነ ከኔፋውያን [a]የተ
ገነጠሉትን ብዙዎች እስከሚያሳፍሩ፣
ኃጢአታቸውን በመናዘዝ ለንስሃ እስከሚ
ጠመቁ፣ እናም የሰሩትን ስህተት ለማረም
ጥረት በማድረግ ወደ ኔፋውያን በፍጥነት
እስከሚመለሱ ድረስ በታላቅ ኃይል ሰብ
ከውላቸው ነበር።
፲፰ እናም እንዲህ ሆነ ኔፊና ሌሂ ይናገሩ
ዘንድ ኃይልና ስልጣን ስለተሰጣቸው፣
እናም ደግሞ ምን [b]መናገር እንዳለባቸው
ስለተሰጣቸው በታላቅ ኃይልና ስልጣን ለላ
ማናውያን ሰበኩ—
፲፱ ስለዚህ በዛራሔምላ ምድር እንዲሁም
በዙሪያው የነበሩት ስምንት ሺህ ላማናው
ያን ለንስሃ እስከሚጠመቁ፣ እናም የአባ
ቶቻቸው ወግ ኃጢያት መሆኑን [c]እስከሚ
ያምኑ ድረስ ላማናውያኑም እጅግ እስኪገ
ረሙ ይናገሩ ነበር።
፳ እናም እንዲህ ሆነ ኔፊና ሌሂ ከዚያ
ቦታ ወደ ኔፊ ምድር ለመሄድ ጉዞአቸውን
ቀጠሉ።
፳፩ እናም እንዲህ ሆነ እነርሱም በላማና
ውያን ወታደሮች ተወሰዱና፣ [d]ወህኒ ቤት፣
አዎን አሞንና ወንድሞቹ በሊምሂ አገል
ጋዮች ተጥለውበት በነበረው በዚሁ ወህኒ
ቤት ተጣሉ።
፳፪ እናም ለብዙ ቀናት ያለምግብ በወህኒ
ቤት ከተጣሉ በኋላ፣ እነሆ ይገድሉአቸው
ዘንድ እነርሱን ለማውጣት ወደ ወህኒ ቤቱ
ሄዱ።
፳፫ እናም እንዲህ ሆነ እንቃጠላለን በማ
ለት እጃቸውን በእነርሱ ላይ ለማሳረፍ እስ
ከሚፈሩ እንኳን ኔፊና ሌሂ [e]እሳት በሚ
መስል ነገር ተከበው ነበር። ይሁን እንጂ፣
ኔፊና ሌሂ አልተቃጠሉም ነበር፤ ልክ በእ
ሳት መካከል የቆሙ ይመስሉ ነበር እናም
አልተቃጠሉም ነበር።
፳፬ እናም [f]በእሳት አምድ መከበባቸውን
እናም እንደማይቃጠሉ በተመለከቱ ጊዜ፣
ልባቸው ተበረታታ።
፳፭ ላማናውያን እጃቸውን ለመጫን እን
ዳልደፈሩ ተመለከቱ፤ አጠገባቸው ለመቅ
ረብም አልደፈሩም፤ ነገር ግን ተደንቀው
ዲዳ የሆኑ በመምሰል ቆሙ።
፳፮ እናም እንዲህ ሆነ ኔፊና ሌሂ ቆሙ፣
እናም ለእነርሱም እንዲህ በማለት መናገር
ጀመሩ፥ አትፍሩ፣ እነሆም እኛን ለመግደል
እጃችሁን በእኛ ላይ ማድረግ እንደማትችሉ
የምታዩትን ይህን አስገራሚ ነገር የሚያሳ
ያችሁ እግዚአብሔር ነው።
፳፯ እናም እነሆ ይህንን ቃላት በተናገሩ
ጊዜ መሬቱ በኃይል ተንቀጠቀጠ፤ እናም
የወህኒ ቤቱ ግድግዳ በመሬት ላይ የተንከ
ባለለ እስከሚመስል ድረስ ተንቀጠቀጠ፤
ነገር ግን እነሆ አልወደቁም። እናም እነሆ
በወህኒ ቤት ውስጥ የነበሩት ላማናውያንና
ተገንጥለው የነበሩት ኔፋውያን ነበሩ።
፳፰ እናም እንዲህ ሆነ በደመና [g]ጭጋግም
ተሸፈኑ፤ እናም አሰቃቂ የሆነ ከባድ ፍርሃት
በእነርሱ ላይ መጣ።
፳፱ እናም እንዲህ ሆነ በደመናው ጭጋግ
ከበላይ በኩል በሚመስል ሁኔታ [h]ድምፅ
እንዲህ ሲል መጣ፥ ንስሃ ግቡ፣ ንስሃ ግቡ፤
እናም መልካም ዜናን ለእናንተ እንዲናገሩ
የላኳቸውን አገልጋዮቼን ለማጥፋት ከእን
ግዲህ አትሹ።

፲፯ *ሀ* ሔለ. ፱፡፱።
፲፰ *ሀ* ት. እና ቃ. ፲፡፲–፲።
ቅ.መ.መ. ትንቢት፣
መተንበይ።
፲፱ *ሀ* ቅ.መ.መ. መቀየር፣
የተቀየረ፣
የሚስዮን ስራ።
፳፩ *ሀ* ሞዛያ ፯፡፲–፲፣ ፳፩፡፳፫።
፳፫ *ሀ* ዘፀአ. ፫፡፪።
፳፬ *ሀ* ዘፀአ. ፲፡፡ ፳፬፣
፳ ኔፊ ፩፡፲፣
ት. እና ቃ. ፳፱፡ ፲፪፣
ጆ.ስ.—ታ. ፩፡ ፲፯።
፳፭ *ሀ* ዘፀአ. ፲፡ ፳።
፳፱ *ሀ* ፫ ኔፊ ፲፩፡ ፫–፲፡።

፴ እናም እንዲህ ሆነ ይህንን ድምፅ በሰሙ ጊዜና፣ የመብረቅ ድምፅ አለመሆኑን፣ ታላቅ የሁካታም ጫጫታ ድምፅ አለመሆኑን ተመለከቱ፤ ነገር ግን እነሆ ፍፁም የሆነ እርጋታ ያለው [ሀ]ለስላሳ ድምፅ ነበር፤ ልክ እንደሹክሹክታ፣ እናም ነፍስንም እንኳን የሚወጋ ነበር—

፴፩ እናም ድምፁ ለስላሳ ቢሆንም፣ እነሆ መሬቱ በኃይል ተንቀጠቀጠ፤ የወህኒ ቤቱ ግድግዳ ወደመሬት የሚወድቅ በመምሰል በድጋሚ ተንቀጠቀጠ፤ እናም እነሆ እነርሱን የሸፈናቸው የደመናም ጭጋግ አልተበተነም ነበር—

፴፪ እናም እነሆ ድምፅ በድጋሚ እንዲህ ሲል መጣ፥ ንስሃ ግቡ፣ ንስሃ ግቡ መንግስተ ሰማያት ቀርባለችና፤ እናም ከእንግዲህ አገልጋዮቼን ለማጥፋት አትሞክሩ። እናም እንዲህ ሆነ መሬት በድጋሚ ተንቀጠቀጠችና፣ ግድግዳው ተናወጠ።

፴፫ እናም ደግሞ ለሶስተኛ ጊዜ በድጋሚ ድምፅ መጣና፣ በሰው ሊነገሩ የማይችሉ አስደናቂ ቃላት ተናገረ፤ እናም ግድግዳው በድጋሚ ተንቀጠቀጠና ምድር ተሰነጣጥቃ የተከፈለች እስከሚመስል ድረስ ተናወጠች።

፴፬ እናም እንዲህ ሆነ የደመናው ጭጋግ ስለሸፈናቸው ላማናውያን ለመሸሽ አልቻሉም፤ አዎን እናም ደግሞ በላያቸው ላይ በመጣው ፍርሃት የተነሳ አይንቀሳቀሱም ነበር።

፴፭ እንግዲህ ከኔፋውያን የተወለደ፣ በአንድ ወቅት በእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን አባል የነበረ ነገር ግን ተለይቶ የሄደ አንድ ሰው በመካከላቸው ነበር።

፴፮ እናም እንዲህ ሆነ በሌላ አቅጣጫ ዞረና፣ እነሆ በደመናው ጭጋግ ውስጥ የኔፊንና የሌሂን ፊት ተመለከተ፤ እናም እነሆ ፊታቸውም ልክ እንደመላዕክት እጅግ [ሀ]ያበራ ነበር። ወደሰማይ ሲመለከቱም ተመለከታቸው፤ እናም ወደሚመለከቱት ፍጡር ድምፃቸውን ከፍ እንደሚያደርጉ ወይም እንደሚነጋገሩ ዓይነት መስለዋል።

፴፯ እናም እንዲህ ሆነ ይህ ሰው ይመለከቱ ዘንድ ወደ ህዝቡ ጮኸ። እናም እነሆ ለመዞርና ለመመልከት ሀይል ስለተሰጣቸው ዞሩና ተመለከቱ፤ እናም የኔፊንና የሌሂን ፊት ተመለከቱ።

፴፰ እናም ለሰውየውም እንዲህ አሉ፥ እነሆ ይህ ሁሉ ነገር ምን ማለት ነው፣ እናስ እነዚህ ሰዎች የሚነጋገሩት ከማን ጋር ነው?

፴፱ እንግዲህ የሰውየው ስም አሚናዳብ ይባል ነበር። እናም አሚናዳብ እንዲህ ሲል ተናገራቸው፥ እነርሱ ከእግዚአብሔር መላእክት ጋር ይነጋገራሉ።

፵ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን እንዲህ አሉት፥ ይህ የጨለማው ጭጋግ እኛን ከመሸፈን ይወገድ ዘንድ [ሀ]ምን እናድርግ?

፵፩ እናም አሚናዳብ እንዲህ አላቸው፥ አልማና፣ አሙሌቅ፣ እናም ዚኤዝሮም ባስተማሯችሁ [ሀ]በክርስቶስም እምነት እስከሚኖራችሁ ድረስ ድምፃችሁን በማንሳት [ለ]ንስሃ መግባት እንዲሁም ማልቀስ ይገባችኋል፤ እናም ይህንን በምታደርጉበት ጊዜ የሸፈናችሁ የጨለማ ጭጋግ ይወገድላችኋል።

፵፪ እናም እንዲህ ሆነ ምድርን በማንቀጥቀጥ ወዳናወጠው ድምፅ ሁሉም መጮህ ጀመሩ፤ አዎን የደመናው ጭጋግ እስከሚበታተን ድረስም ጮኹ።

፵፫ እናም እንዲህ ሆነ አይኖቻቸውን ወዲህና ወዲያ አዞሩ፣ እናም የደመናው ጭጋግ ለቋቸው መሄዱን ተመለከቱ፣ እነሆ እነርሱ፣ አዎን፣ እያንዳንዱ ነፍስ በእሳቱ አምድ [ሀ]መከበቡን ተመለከተ።

፵፬ እናም ኔፊና ሌሂ በላማናውያን መካከል ነበሩ፤ አዎን ተከበው ነበር፤ አዎን፣ ልክ በሚነድ ነበልባል መካከል እንዳሉ ነበር፤ ይሁን እንጂ እነርሱን የሚጎዳም ሆነ የወህኒ ቤቱን ግድግዳ የሚያቃጥል አልነ

፴ሀ ፩ ነገሥ. ፲፱፥ ፲፪፤
ት. እና ቃ. ፹፭፥ ፮።
፴፮ሀ ዘፀአ. ፴፬፥ ፳፱–፴፭፤
የሐዋ. ፮፥ ፲፭።
፵ሀ የሐዋ. ፪፥ ፴፯–፴፱።
፵፩ሀ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
ለ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣ ንስሀ መግባት።
፵፫ሀ ፫ ኔፊ ፲፯፥ ፳፬፤ ፲፱፥ ፲፬።

በረም፤ እናም ለመናገር በሚያዳግት እን ዲሁም በክብር በተሞላ ᵐደስታ ተሞልተው ነበር።

፶፭ እናም እነሆ፣ የእግዚአብሔር ᵐቅዱስ መንፈስ ከሰማይ መጣና፣ ወደ ልባቸው ገባ፣ እናም በእሳት የተሞሉ ይመስል ነበር፣ አስደናቂ ቃላትንም ᵃመናገር ይችሉ ነበር።

፶፮ እናም እንዲህ ሆነ አንድ ድምፅ፣ አዎን የሚያምር ድምፅ፣ ልክ እንደሹክ ሹክታ እንዲህ ሲል መጣ፡

፶፯ ከዓለም መፈጠር ጀምሮ በነበ ረው በተወዳጁ ባላችሁ እምነት ምክንያት ᵐሰላም፣ ሰላም ለእናንተ ይሁን።

፶፰ እናም እንግዲህ ይህንን በሰሙ ጊዜ ድምፁ ከመጣበት ቦታ ለመመልከት ዐይና ቸውን ወደ ላይ አነሱ፤ እናም እነሆ ᵐሰማይ ሲከፈት ተመለከቱ፤ መላዕክትም ከሰማይ መጡና አገለገሏቸው።

፶፱ እናም እነዚህን ነገሮች ያዩና የሰሙ ወደ ሶስት መቶ የሚጠጉ ነፍሳት ነበሩ፤ እናም እንዲሄዱና፣ እንዳይገረሙ፣ እናም እንዳይጠራጠሩ ታዘዙ።

፷ እናም እንዲህ ሆነ እነርሱም ሄዱ፤ እናም ለህዝቡ ተናገሩ፣ በምድሪቱም ዙሪያ ሁሉ ባጠቃላይ ስለተመለከቱት እንዲሁም ስለ አዩአቸው ነገሮች በሙሉ ተናገሩ፤ የተቀበ ሉት መረጃ ታላቅ በመሆኑ ብዙዎች ላማና ውያን በእነርሱ ተቀይረው ነበር።

፷፩ እናም ብዙዎች ᵐያመኑትም የጦር መሳሪያዎቻቸውንና፣ ደግሞ ጥላቻቸው ንና የአባቶቻቸውን ወግ ተዉ።

፷፪ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን ለኔፋ ውያን ምድራቸውን ተዉላቸው።

ምዕራፍ ፯

ፃድቃን የሆኑት ላማናውያን ለኃጢአተ ኞቹ ኔፋውያን ሰበኩላቸው—ሁለቱም በሰላሙና በጥጋቡ ዘመን በለፀጉ—የኃ ጢያት ደራሲው፣ ሉሲፈር፣ የኃጢአተኞ ችን፣ እናም የጋድያንቶንን ዘራፊዎች በግ ድያና በክፋት ልባቸውን አነሳሳ—ዘራፊ ዎቹ የኔፋውያንን መንግስት ተቆጣጠሩ። ከ፳፩–፳፫ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ የመሣፍንቱ ስልሳ ሁለተኛው ዓመት የንግስና ዘመን በተፈፀመ ጊዜ፣ እነዚህ ነገሮች ሁሉ ሆኑ፣ እናም አብ ዛኞቹ ላማናውያን ᵐፃድቃኖች ሆነው በእም ነታቸው ብርታት እንዲሁም ፅኑነት ፅድቃ ቸው ከኔፋውያን ይበልጥ ነበር።

፪ እነሆም ብዙ ኔፋውያን ᵐጠጣሮች፣ እን ዲሁም ንስሃ የማይገቡ፣ እናም በአጠቃላይ ክፉዎች ነበሩ፤ በዚህም የተነሳ በመካከላ ቸው የመጡትን የእግዚአብሔርን ቃልና፣ ሁሉንም ስብከትና፣ ትንቢት አልተቀበ ሉም ነበር።

፫ ይሁን እንጂ፣ በላማናውያን መለወጥ የተነሳ፣ አዎን፣ በመካከላቸው በተቋቋመ ችው የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ምክ ንያት የቤተክርስቲያኗ ሰዎች ታላቅ ደስታ ነበራቸው። እናም እርስ በእርሳቸው ᵐበመ ተባበር፣ እናም አንደኛው ሌላኛውን አስደ ሰቱ፣ ታላቅ ደስታም ነበራቸው።

፬ እናም እንዲህ ሆነ ብዙ ላማናውያን ወደ ዛራሔምላ ምድር መጡና፣ ለኔፋው ያን ሰዎች ᵐስለመለወጣቸው ተናገሩ፣ እም ነት እንዲኖራቸውም እንዲሁም ንስሃ እን ዲገቡ አጥብቀው መከሯቸው።

፭ አዎን፣ እናም አብዛኛዎቹ ብዙዎቹን የእግዚአብሔርና የበጉ ትሁት ተከታዮች እንዲሆኑ ወደ ጥልቅ ትህትና ለማምጣት በታላቅ ኃይልና ስልጣን ሰበኩላቸው።

፮ እናም እንዲህ ሆነ ብዙዎቹ ላማናው ያን በምድሪቱ ᵐበስተሰሜን በኩል ተጓዙ፤ እናም ደግሞ ኔፊና ሌሂ ህዝቡን ለመስበክ

ᵃ፶፩ ሀ ቅ.መ.መ. ደስታ።
ᵇ፶፭ ሀ ᶜ ኔፊ ፱፡፳፣ ፳፣ ኤተር ፲፪፡፲፡፲፩።
ለ ቅ.መ.መ. የመንፈስ ስጦታዎች።
ᵃ፶፯ ሀ ቅ.መ.መ. ሰላም።
ᵇ፶፰ ሀ ᶜ ኔፊ ፩፡፰፡፰።
ᵃ፶፱ ሀ አልማ ፴፭፡፭።
ᵃ፮ ᶜ፩ ሀ ሔለ. ፲፫፡፩።
ᵇ፪ ሀ ሮሜ ፩፡፳፰–፴፪።
ᶜ ሀ ቅ.መ.መ. ጓደኝነት።
ᵃ፬ ሀ ቅ.መ.መ. መቀየር፣ የተቀየረ።
ᵃ፮ ሀ አልማ ፳ᶜ፡፭፡፬–፱፣ ሔለ. ᶜ፡፲፩–፲፪።

በምድሪቱ በስተሰሜን በኩል ተጓዙ። እናም ስልሳ ሦስተኛው ዓመት እንደዚህ ተፈፀመ።

፯ እናም እነሆ በምድሪቱ ሁሉ ሰላም ሆነ፤ በዚህም የተነሳ ኔፋውያን ወደፈለጉት ማን ኛውም ስፍራ፣ ከኔፋውያንም ሆነ ከላማና ውያን ጋር ተጓዙ።

፰ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያንም ደግሞ ከላማናውያንም መካከል ሆነ ከኔፋውያን መካከል መሄድ በፈለጉበት ስፍራ ሁሉ ሄዱ፤ እናም አንዳቸው ከሌላኛቸው ጋር ለመግዛት እንዲሁም ለመሸጥ እንዲሁም እንደፍላጎታቸው ጥቅም ለማግኘት ነፃ ግን ኙነት ነበራቸው።

፱ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያንም ሆኑ ኔፋውያን እጅግ ሀብታም ሆኑ፤ እናም በም ድሪቱ በስተደቡብም ሆነ በስተሰሜን የተ ትረፈረፈ ወርቅና፣ ብር እንዲሁም የከበሩ ብረቶች በብዛት ነበሩአቸው።

፲ እንግዲህ የምድሪቱ ደቡቡ ክፍል ሌሂ ተብሎ ይጠራ ነበር፤ እንዲሁም የምድሪቱ ሰሜኑ ክፍል በሴዴቅያስ ልጅ ስም ሙሌቅ ተብሎ ይጠራ ነበር፤ ምክንያቱም ጌታ ᐸሙሌቅን በምድሪቱ በሰሜን በኩል እን ዲሁም ሌሂን በደቡብ በኩል አምጥቷቸ ዋልና።

፲፩ እናም እነሆ በእነዚህ በሁለቱም ቦታ ዎች ሁሉም ዓይነት ወርቅና፣ ከሁሉም ዓይነት ብር እንዲሁም የከበረ አፈር ነበር፤ እናም ደግሞ በጥንቃቄ የሚሰሩ፣ ሁሉንም ዓይነት አፈር የሚሰሩና የሚያጣሩ ነበሩ፤ ሀብታሞችም ሆኑ።

፲፪ እህልም በብዛት በስተሰሜን እንዲሁም በስተደቡብ አበቀሉ፤ እናም በደቡብም እን ዲሁም በሰሜን በለፀጉ፤ እናም በምድሪቱ ተባዙ እንዲሁም እጅግ በረቱ። እናም ብዙ መንጋዎችንና ከብቶችን አዎን በብዛት ጠቦ ቶችን አረቡ።

፲፫ እነሆ ሴቶቻቸው ጥረዋልና፣ ፈትለ ዋል፣ እናም ሁሉንም የተፈተለ ጥሩ በፍታ ዓይነት ልብሶችና እርቃናቸውን ለመሸፈን ማንኛውንም ዓይነት ልብስ አዘጋጅተዋል። እናም ስልሳ አራተኛው ዓመት በሰላም እን ደዚህ አለፈ።

፲፬ እናም በስልሳ አምስተኛውም ዓመት ደግሞ ታላቅ ደስታና ሰላም፣ አዎን ብዙ ስብከትና የሚመጣውን በተመለከተ ብዙ ትንቢቶች ነበሯቸው። እናም ስልሳ አምስ ተኛው ዓመት እንደዚህ ተፈፀመ።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ በመሣፍንቱ ስልሳ ስድስተኛ ዓመት የንግስ ዘመን፣ እነሆ ᐸሴዞራም ባልታወቀ ሰው በፍርድ ወንበሩ ተቀምጦ ሳለ ተገደለ። እናም እንዲህ ሆነ በዚሁ ዓመት፣ በእርሱ ምትክ በህዝቡ የተ ሾመው ወንድ ልጁ ደግሞ ተገደለ። ስልሳ ስድስተኛው ዓመትም እንደዚህ ተፈፀመ።

፲፮ እናም በስልሳ ሰባተኛው ዓመት መጀ መሪያ ላይ ህዝቡ በኃጢያት እጅግ ማደግ ጀመረ።

፲፯ እነሆም ጌታ ለቁጣ፣ ለጦርነትም፣ ይሁን ለደም መፋሰስ እንዳይነሳሱ በም ድራዊ ሀብት ለብዙ ጊዜ ባረካቸው፤ ስለ ዚህ ልባቸውን በሀብታቸው ላይ ማድረግ ጀመሩ፤ አዎን በድጋሚም አንዳቸው በሌ ላኛቸው ላይ እራሳቸውን ከፍ ለማድረግ ፈለጉ፤ ስለዚህ ያገኙም ዘንድ ᐸበድብቅ ግድያን፣ እናም ስርቆትን እንዲሁም ዝር ፊያን መፈፀም ጀመሩ።

፲፰ እናም አሁን እነሆ የገዳዮቹና የዘራፊ ዎቹ ቡድን በቂሽቁመን እንዲሁም ᐸጋድ ያንቶን የተቋቋሙት ነበሩ። እናም እንግ ዲህ እንዲህ ሆነ ከጋድያንቶን ቡድን ከኔ ፋውያንም መካከል ብዙዎች ነበሩ። ነገር ግን እነሆ ኃጢአተኞች ከሆኑት ላማናውያን መካከል በቁጥር ብዙ ነበሩ። እናም የጋድ ያንቶን ሌቦች እንዲሁም ገዳዮች ተብለው ይጠሩ ነበር።

፲፱ እናም እነርሱ ናቸው ዋናውን ዳኛ ሴዞራምን እንዲሁም ልጁን በፍርድ ወን በሩ ላይ እንዳለ የገደሉት፤ እናም እነሆ፣ ማናቸውም አልተገኙም ነበር።

፲ ᐸ ሞዛያ ፳፭፡፪–፬፤ ሔለ. ፭፡፳፡፩። ፲፭ ᐸ ሔለ. ፭፡፩። ፲፰ ᐸ ሔለ. ፪፡፬፣ ፲፪–፲፫።
ሔለ. ፭፡፳፭፡፩። ፲፯ ᐸ ፫ ኔፊ ፱፡፱–፲፡

፳ እናም እንግዲህ እንዲህ ሆነ ላማናውያን በመካከላቸው ሌቦች እንዳሉ ባወቁ ጊዜ እጅግ አዘኑ፤ እናም ከምድረ ገፅ እነርሱን ለማጥፋት በኃይላቸው ማንኛውንም መን ገድ ተጠቀሙ።

፳፩ ነገር ግን እነሆ ሰይጣን የአብዛኞ ቹን የኔፋውያን ልብ አነሳሳ፤ በዚህም የተ ነሳ ከሌቦቹ ቡድን ጋር በግድያቸው እንዲ ሁም በዝርፊያቸውና በስርቆታቸው እን ዳይሰቃዩ፣ በማንኛውም አስቸጋሪ ሁኔታ ቢቀመጡ እርስ በራስ እንዲረዳዱ፣ ከእነ ርሱ ጋር ተቀላቀሉ እናም ወደ እነርሱ ቃል ኪዳን እንዲሁም መሃላ ገቡ።

፳፪ እናም እንዲህ ሆነ የራሳቸው ምል ክቶች ነበሩአቸው፤ አዎን፣ [ሀ]ሚስጥራዊ ምልክትና፣ ሚስጥራዊ ቃላት፤ እናም ይህንም ያደረጉት ወደ ቃል ኪዳኑ የገባ ውን ወንድም ይለዩበት ዘንድ፣ አባሉ ኃጢ ያት የሆነን ማንኛውንም ነገር ቢያደርግ ቃል ኪዳን በገባው በወንድሙም ሆነ በቡድኑ እንዳይጎዱ ዘንድ ነበር።

፳፫ እናም ከሀገራቸው ህግጋት እንዲ ሁም ደግሞ ከእግዚአብሔር ህግጋት ጋር ተቃራኒ የሆኑትን ግድያዎችና፣ ዝርፊያ ዎች፣ እናም ስርቆትና፣ ዝሙትን እንዲ ሁም ሁሉንም ዓይነት ክፋት እንደዚህ ለመ ፈፀም ይችሉ ዘንድ።

፳፬ እናም ከእነርሱ ቡድን የሆነ ማንኛ ውም ሰው ለዓለም [ሁ]ኃጢአታቸውን እን ዲሁም እርኩሰታቸውን ቢገልፅ፤ እንደ ሀገራቸው ህግ ሳይሆን በጋድያንቶን እና በቂሽቁመን በተሰጡት የክፋታቸው ህግጋት መሰረት ለፍርድ ይቀርባል።

፳፭ እናም እነሆ፣ ይህ ሚስጥራዊ [ሀ]መሃ ላና ቃል ኪዳን አልማ ለልጁ ህዝቦችን ወደ ጥፋት የሚወስድ ዘዴ እንዳይሆን በመፍ ራቱ ወደ ዓለም እንዳይሄድ ያዘዘበት ነው።

፳፮ እንግዲህ እነሆ እነዚህ [ሀ]ሚስጥራዊ መሃላዎችና ቃል ኪዳኖች ለሔለማን ከተ ሰጡት መዛግብት ለጋድያንቶን አልመ ጡም፤ ነገር ግን እነሆ፣ የተከለከለውን ፍሬ እንዲቀምሱ የመጀመሪያ ቤተሰቦቻችንን ያታለለው [ሀ]ያው ፍጡር እነዚህን በጋድያን ቶን ልብ ውስጥ አስቀምጦ ስለነበር ነው—

፳፯ አዎን ወንድሙን አቤልን ቢገድለው ዓለም እንደማያውቀውም [ለ]ካቃየን ጋር ያሴረው ይኸው ፍጡር ነበር። እናም እር ሱም ከቃየንና ከተከታዮቹ ጋር ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አሴረ።

፳፰ ደግሞም ረጅም ግንብ [ሀ]ገንብተው ሰማይ መድረስን በሰው ልጆች ልብ ውስጥ ያደረገውይህ ፍጡር ነው። እናም እነዚያን ሰዎች ከግንቡ ወደዚህ ምድር የመጡትን የገፋፋቸው፤ [ሀ]ፍፁም ወደሆነ ጥፋት እናም ዘለዓለማዊ ወደሆነው ገሃነም እስከሚጎት ታቸው ድረስ የጨለማን እንዲሁም የእር ኩሰትን ስራ በምድር ገፅ እንዲበተን ያደ ረገውም ይኸው ፍጡር ነው።

፳፱ አዎን፣ አሁንም የጨለማውን ስራ እንዲሁም ሚስጥራዊ ግድያውን እንዲያ ደርግ [ሀ]በጋድያንቶን ልብ ውስጥ ያስገባውም ይህ ፍጡር ነው፤ እናም ከሰው ልጅ መፈ ጠር ጀምሮ እስከዚህ ጊዜ ድረስ ይህን ያመ ጣው ይኸው ፍጡር ነው።

፴ እናም እነሆ [ሀ]የኃጢያት ሁሉ ደራሲው እርሱ ነው። እናም እነሆ፣ እርሱም የጨለ ማውን ስራ እንዲሁም ሚስጥራዊ ግድያ ውን ቀጥሎበታል፣ እንዲሁም በሰው ልጆች ልብ ላይ ተፅዕኖ ማድረግ እስከቻለ ይህ ንን ሴራ፣ መሃላቸውንና ቃል ኪዳናቸውን እንዲሁም ይህንን አሰቃቂ የኃጢያት ዓላማ ከትውልድ እስከ ትውልድ ያስተላልፋል።

፴፩ እናም እንግዲህ እነሆ፣ በኔፋውያን ልብ ላይ ታላቅ የሆነ ተፅዕኖ አግኝቷል፤ አዎን፣ ስለዚህም እነርሱ እጅግ ኃጢአተ ኞች ሆነዋል፤ አዎን፣ ብዙዎቹም ከፅድቅ

፳፪ [ሀ] ቅ.መ.መ. የሚስጥር ስብሰባ።
፳፫ [ሀ] ቅ.መ.መ. ክፉ፣ ክፋት።
፳፭ [ሀ] አልማ ፴፯፡ ፳፯–፴፪።
፳፯ [ሀ] ሙሴ ፭፡ ፳፱፣ ፴፱–፴፪።
[ለ] ፲ ኔፊ ፤ ፳፳፣

ሙሴ ፬፡ ፯–፲፪።
፳፯ [ሀ] ሙሴ ፭፡ ፲፳–፴፣ ።
፳፰ [ሀ] ዘፍጥ. ፲፩፡ ፩–፬፣
ኤተር ፩፡ ፣ ።
[ለ] ኤተር ፳፡ ፱፣ ፲፭–፳፭።

፳፱ [ሀ] ሔለ. ፪፡ ፬–፲፣ ።
፴ [ሀ] አልማ ፭፡ ፴፱–፴፪፣
ሞሮኒ ፯፡ ፲፪፣ ፲፯፣
ሙሴ ፪፡ ፬።

ጎዳና ርቀዋል፤ እንዲሁም የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት በእግራቸው ስር ʺረግጠውታል፤ እናም በራሳቸው አመለካከት ሄደዋል፤ እናም ከወርቆቻቸው እንዲሁም ከብራቸው ለራሳቸው ጣኦቶችን ሰርተዋል።

፴፪ እናም እንዲህ ሆነ እነዚህ ሁሉ ክፋቶች በእነርሱ ላይ የመጡት ʺበረጅም ጊዜ ውስጥ አይደለም፤ ስለዚህ አብዛኛዎቹ ክፋቶች የሆኑት በኔፊ ህዝብ ላይ በመሣፍንቱ ስልሳ ሰባተኛ ዓመት የንግስና ዘመን ውስጥ ነበር።

፴፫ እናም ለፃድቃኖች ታላቅ ሀዘን እንዲሁም ለቅሶ፣ በስልሳ ስምንተኛው ዓመት ደግሞ በክፋታቸው ጨመሩ።

፴፬ እናም ላማናውያን በአምላካቸው እውቀት ማደግ፣ አዎን እነርሱ ስርዓቶችንና ትዕዛዛቱን መጠበቅ፣ እናም በፊቱም በእምነት እንዲሁም በቀጥታ መራመድ በጀመሩበት ጊዜ፣ ኔፋውያን እምነት አጥተው መመንመን እንዲሁም በክፋትና በእርኩሰት ማደግ መጀመራቸውን እንደዚህ እንመለከታለን።

፴፭ እናም በኃጢአታቸውና ልባቸውን በማጠጠራቸው የተነሳ የጌታ መንፈስ ከኔፋውያን ʺመለየት እንደጀመረ እንመለከታለን።

፴፮ እናም ላማናውያን የማያስቸግሩና ቃሉን ለማመን ፈቃደኞች በመሆናቸው ጌታ ከመንፈሱ በላያቸው ላይ ማፍሰስ መጀመሩን ተመለከትን።

፴፯ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን የጋድያንቶንን የዘራፊዎች ቡድን አደኑ፤ እናም ይበልጥ ኃጢአተኞች በሆኑትም መካከል የእግዚአብሔርን ቃል ሰበኩ፤ ስለዚህ እነዚህ የዘራፊዎች ቡድን ከላማናውያን መካከል ፈፅመው ጠፉ።

፴፰ እናም እንዲህ ሆነ በሌላ በኩል እጅግ ኃጢአተኛ ከሆኑት ጀምሮና ፃድቃን የሆኑት አብዛኞቹም በስራቸው እስከሚያምኑና፣ ከዘረፉት እስከሚካፈሉ፣ እናም በሚስጥራዊው ግድያቸውና፣ ቅንጅታቸው ከእነርሱ ጋር እስከሚገናኙ ድረስ በማባበል፤ ኔፋውያን እነርሱን አሳደጓቸውና ደገፏቸው።

፴፱ እናም እንደዚህ ብቸኛውን የመንግስት አስተዳደር አገኙ፤ ʺበድሆች እንዲሁም በየዋሆች እንዲሁም ትሁት የእግዚአብሔር ተከታዮች ላይ ጀርባቸውን መለሱባቸው፣ በእግራቸውም ሥር ረገጡአቸው፣ እናም መቱአቸውና፣ አሰቃዩአቸው።

፵ እናም በአሰቃቂ ሁኔታ እንዲሁም ለዘለዓለማዊው ጥፋት ʺመዳረሳቸውን ተመለከትን።

፵፩ እናም እንዲህ ሆነ በኔፊ ህዝብ ላይ የመሣፍንቱ ስልሳ ስምንተኛ ዓመት የንግስና ዘመን ተፈፀመ።

የሔለማን ልጅ የኔፊ ትንቢት—ለኃጢአታቸው ንስሃ ካልገቡ የኔፊን ህዝብ እግዚአብሔር ፍፁም ለማጥፋት በቁጣው እንደሚጎበኛቸው አስፈራራቸው። እግዚአብሔር የኔፊን ህዝብ በቸነፈር መታ፤ ንስሃ ገቡ እናም ወደ እርሱ ተመለሱ። ላማናዊው ሳሙኤል ለኔፋውያን ተነበየ።

ከምዕራፍ ፯ እስከ ፲፮ አጠቃሎ የያዘ።

ምዕራፍ ፯

ኔፊ በሰሜን ተቀባይነትን አላገኘም እናም ወደዛራሔምላ ተመለሰ—በአትክልቱ ስፍራ ግንብ ላይ ፀሎት አደረገ፣ እናም ለህዝቡ ንስሃ እንዲገቡ አለበለዚያም እንደሚጠፉ ተናገረ። ከ፳፫–፳፩ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እነሆ እንግዲህ እንዲህ ሆነ በኔፊ ህዝብ ላይ በመሣፍንቱ ስልሳ ዘጠነኛ የንግስና ዘመን የሔለማን ልጅ ኔፊ፣ ከምድሪቱ

፴፩ሀ ፩ ኔፊ ፲፱፥ ፯።
፴፪ሀ አልማ ፵፮፥ ፰።
፴፭ሀ ሞዛያ ፪፥ ፴፮፤
ት. እና ቃ. ፻፳፩፥ ፴፯።
፴፱ሀ መዝ. ፻፱፥ ፲፮፤
አልማ ፭፥ ፶፬–፶፮፤
ት. እና ቃ. ፶፮፥ ፲፮።
፵ሀ ሔለ. ፭፥ ፪፤ ፲፩፥ ፴፯፤
ት. እና ቃ. ፲፰፥ ፮።

በስተሰሜን በኩል ወደ ዛራሔምላ ምድር
ᵐተመለሰ።
፤ በምድሪቱ በስተሰሜን በኩል ከነበሩት
ሰዎች መካከል ነበር፣ እናም የእግዚአብሔ
ርን ቃል ለእነርሱ እየሰበከ፣ እናም ብዙ ነገ
ሮችን ለእነርሱ እየተነበየ ነበርና፤
፫ እናም ቃሉን ሁሉ አልተቀበሉትም
ነበር፤ ስለዚህ ከእነርሱ ጋር መቆየት አል
ቻለም ነበር፤ ነገር ግን በድጋሚ ወደ ትው
ልድ ስፍራው ተመለሰ።
፬ እናም ህዝቡ በአሰቃቂው ኃጢያት
መሆናቸውን እንዲሁም የጋድያንቶን ሌቦች
የፍርድ ወንበሩን መያዛቸውን—በምድሪ
ቱም ላይ ያለአግባብ ኃይልና ስልጣኑን
በማግኘታቸው፣ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ
ወደጎን በመተዋቸው፣ እናም በፊቱም በት
ንሽም እንኳን መልካምን ባለማድረጋቸው፤
ለሰው ልጆችም በጻድቅ ባለመፍረዳቸው
በመምልከት፤
፭ ፃድቃኖችንም ፃድቃን በመሆናቸው
በመኮነን፤ ጥፋተኞችን፣ እንዲሁም ክፉ
ዎችን በገንዘባቸው ያለቅጣት እንዲሄዱ
በመፍቀዳቸው፤ እናም ከዚህ በተጨማሪ
በስልጣን የበላይ በመሆን በመቀጠል እን
ዲገዙ እንደፍቃዳቸው ለመስራት ጥቅም
ንና ᵐየዓለም ክብርን ያገኙ ዘንድ፣ እናም
ከዚህ በተጨማሪ፣ በቀላሉ ዝሙትን እን
ዲፈፅሙና፣ ይሰርቁና፣ ይገድሉ፣ እናም
እንደፈቃዳቸው ይፈፅሙ ዘንድ በመፍቀ
ዳቸው—
፮ እንግዲህ ብዛት በሌላቸው ጊዜአት
ውስጥ ይህ ታላቅ ኃጢያት በኔፋውያን ላይ
መጣ፤ እናም ኔፊ ይህንን በተመለከተ ጊዜ
ልቡ በደረቱ ውስጥ በሀዘን ተሞልቶ ነበር፤
እናም በነፍሱም ስቃይ ተናገረ፥
፯ አቤቱ አባቴ ኔፊ ከኢየሩሳሌም ምድር
ለመጀመሪያ በመጣ ጊዜ መኖር ብችል
እመኝ ነበር፤ በቃል ኪዳኑም ምድር ከእርሱ
ጋር ለመደሰት ይቻለኝ ነበር፤ የእርሱ ሰዎ
ችን በቀላል ልመናን ያዳምጡ፣ የእግዚአ
ብሔርን ትዕዛዛት በመጠበቅ ፅኑ፣ እናም
ክፉትን ለመስራት የማይቸኩሉ ነበሩ፤
እናም የጌታን ቃላት ለማዳመጥ ፈጣኖች
ነበሩ—
፰ አዎን፣ ቀናቶቼ በነዚያ ዘመናት ለመ
ሆን ቢችሉ ኖሮ ነፍሴ በወንድሞቼ ፅድቅ
ትደሰት ነበር።
፱ ነገር ግን እነሆ፣ እነዚህ የእኔ ቀናት እን
ዲሆኑ ተደርገዋል፣ እናም ነፍሴ በዚህ በወ
ንድሞቼ ክፋት የተነሳ በሀዘን ትሞላለች።
፲ እናም እነሆ እንግዲህ እንዲህ ሆነ ይህም
ወደ ዋናው ገበያ በሚያመራው አውራ
ጎዳና፣ በዛራሔምላ ከተማ በነበረው በአ
ትክልት ስፍራው ግንብ ላይ ነበር፤ ስለዚህ
ኔፊ በአትክልት ስፍራው በሚገኘው ግንብ
አጎንብሶ ነበር፣ ግንቡም ደግሞ ወደ አውራ
ጎዳናው በሚያመራው በመግቢያ በር አጠ
ገብ ነበር።
፲፩ እናም እንዲህ ሆነ አንዳንድ ሰዎች
በሚያልፉበት ወቅት ኔፊ በግንቡ ላይ ሆኖ
ነፍሱን ለእግዚአብሔር ሲያፈስ ተመለ
ከቱ፤ እናም ሮጡና፣ ለህዝቡ ምን እንደ
ተመለከቱ ተናገሩ፣ ህዝቡም በዚህ ህዝብ
ክፋት ታላቅ የሆነው ሀዘኑን ምክንያት
ያውቁ ዘንድ በአንድ ላይ በመሆን መጡ።
፲፪ እናም አሁን ኔፊ በተነሳበት ጊዜ ብዙ
ሰዎች በአንድነት ተሰብስበው ተመለከተ።
፲፫ እናም እንዲህ ሆነ አፉንም በመክፈት
እንዲህ ብሎ ተናገረ፥ እነሆ፣ ᵐለምንድን
ነው ራሳችሁን የሰበሰባችሁት? ስለክፋታ
ችሁ እነግራችሁ ዘንድ ነው?
፲፬ አዎን በታላቅ ክፋታችሁም ምክን
ያት ልቤ እጅግ በማዘኑ፣ ለአምላኬ ነፍ
ሴን አፈስ ዘንድ በግንቤ ላይ ቆሜአለሁ!
፲፭ እናም በሀዘኔ እንዲሁም በልቅሶዬም
ምክንያት በአንድነት ተሰብስባችኋልና፣
ተደንቃችኋል፤ አዎን፣ እናም ለመደነቅ
እጅግ ያስፈልጋችኋል፤ አዎን፣ መገረምን
ይገባችኋል ምክንያቱም ዲያብሎስ በልባ
ችሁ ታላቅ ስፍራን በመያዙ ራሳችሁን ሰጥ
ታችሁታል።
፲፮ አዎን፣ ነፍሳችሁን ወደ ዘለዓለማዊው

ᵐ ፩ ሀ ሔሌ. ፤ ፤።
ᵐ ሀ ማቴ. ፲፫ ፡ ፳፪፤ ፲፮ ፡ ፳፯።
ᵐ ሀ ማቴ. ፫ ፡ ፩–፳።

ስቃይ እንዲሁም መጨረሻ ወደ ሌለው ዋይታ እንዲወረውር ለሚፈልገው መንገ ድስ እንዴት አድርጋችሁ ትሰጡታላችሁ?

፲፯ አቤቱ ንስሃ ግቡ፣ ንስሃ ግቡ! ᵐለምን ትሞታላችሁ? ወደ ጌታ አምላካችሁ ተመ ለሱ፣ ተመለሱ። ለምንስ እርሱ ይተዋች ኋል?

፲፰ ይህም ምክንያቱ ልባችሁን ስላጠ ጠራችሁ ነው፣ አዎን ᵐየመልካሙን እረኛ ድምፅ አታዳምጡምም፤ አዎን በእናንተም ላይ እንዲቆጣ ᵃአነሳስታችሁታል።

፲፱ እናም እነሆ እናንተን ᵐከመሰብሰብ፣ ንስሃን የማትገቡ ከሆነ እነሆ ለውሾች እን ዲሁም ለዱር አውሬዎች ስጋ እስከምትሆኑ ድረስ እናንተን ይበትናችኋል።

፳ አቤቱ፣ እርሱ ባዳናችሁ በዚያው ቀን አምላካችሁን እንዴት ልትረሱት ቻላችሁ?

፳፩ ነገር ግን እነሆ፣ ይህ ጥቅምን ለማግ ኘት ነው፣ በሰዎችም ለመሞገስ፣ አዎን፣ እናም ወርቅና ብርንም ታገኙ ዘንድ ነው። እናም ልባችሁን በሀብት እንዲሁም በዚህ ᵐበዓለም ከንቱ ነገሮች ላይ አድርጋች ኋል፤ ለዚህም ገድላችኋልም፣ ዘርፋችኋ ልም፣ ሰርቃችኋልም፣ እንዲሁም በጎረቤ ቶቻችሁ ላይ ᵃበሀሰት ምስክር ሆናችኋል፤ እናም ሁሉንም ዓይነት ክፋት ፈፅማችኋል።

፳፪ እናም በዚህም ምክንያት ንስሃ ካል ገባችሁ ዋይታ በእናንተ ላይ ይመጣል። ንስሃ የማትገቡ ከሆነ፣ እነሆ፣ ይህች ታላቅ ከተማ፣ እናም በዙሪያው ያሉት፣ በእኛ የተያዙት እነዚያ ታላላቅ ከተሞች ሁሉ ይወሰዱባችኋል፣ በእነርሱም ሥፍራ አይ ኖራችሁም፤ እነሆም ጠላቶቻችሁን ለመ ቋቋም ቀደም ሲል እንዳደረገው ጌታ ᵐብር ታትን አይሰጣችሁም።

፳፫ እነሆም ጌታ እንዲህ ይላል፡ ለኃጢ አታቸው ንስሃ ከገቡት እናም ቃሌን ካዳ መጡት በቀር ለሌሎች ከአንዱ ኃጢአት ይበልጥ ለሌላው ኃይሌን አላሳይም። ስለ ዚህ አሁን፣ ወንድሞቼ ንስሃ ካልገባችሁ፣ ከእናንተ ይልቅ ላማናውያን ᵐእንደሚሻል ላቸው እንድታዩ እፈልጋለሁ።

፳፬ እነሆም፣ እናንተ በተቀበላችሁት ታላቅ እውቀት ላይ ኃጢያትን ባለመፈ ፀማቸው እነርሱ ከእናንተ የበለጠ ፃድቃን ናቸው፤ ስለዚህ ንስሃ ካልገባችሁ ᵐፈፅሞም በምትጠፉበትም ጊዜ እንኳን ጌታ ለእነርሱ መሃሪ ይሆናል፤ አዎን ዘመናቸውን ᵃያራዝ ማል፣ ዘራቸውንም ያበዛል።

፳፭ አዎን፣ በመካከላችሁ ባለው ታላቅ እርኩሰት የተነሳ ለእናንተ ወዮውላችሁ፤ እናም አዎን በጋድያንቶን በተቋቋመው ᵐሚስጥራዊ ቡድን ራሳችሁን አንድ አድ ርጋችኋል!

፳፮ አዎን፣ እጅግ ᵐሀብታም በመሆና ችሁ፣ ከመልካሙም ባሻገር ከፍ እንዲያ ደርጋችሁ ወደ ልባችሁ እንዲገባ ባደረጋ ችሁት ኩራት የተነሳ ᵃዋይታ በእናንተ ላይ ይመጣል!

፳፯ አዎን፣ በክፋታችሁ እንዲሁም በእር ኩሰታችሁ የተነሳ ዋይታ ይሁንባችሁ!

፳፰ እናም ንስሃ ካልገባችሁ ትጠፋላ ችሁ፤ አዎን፣ ምድራችሁም ከእናንተ ትወሰዳለች፣ እናም ከምድረ ገፅ ትጠፋ ላችሁ።

፳፱ እነሆ አሁን፣ እነዚህን ነገሮች በራሴ ይሆናሉ አልልም፣ ምክንያቱም እነዚህን ነገሮች በራሴ አይደለም የማውቃቸው፤ ነገር ግን እነሆ ጌታ እግዚአብሔር እነዚ ህን ᵐነገሮች እንዳውቅ ስላደረገኝ እውነት መሆናቸውን አውቃለሁ፣ ስለዚህ እነርሱ እንደሚሆኑም እመሰክራለሁ።

፲፯ ᴼ ሕዝ. ፲፰፡ ፳፫፣ ፴፭–፴፱።
፲፰ ᴼ ሕዝ. ፴፡ ፲፪፣
ዮሐ. ፣ ፡ ፲፡–፲፮፣
አልማ ፭ ፡ ፴፰–ማ፭፡ ፶፯–፰።
ቅ.መ.መ. መልካሙ እረኛ።
ᴬ ያዕቆ. ፩ ፡ ፰፣
አልማ ፲፪ ፡ ፴፭–ማ፭።
፲፱ ᴼ ᴱ ኔፊ ፣ ፡ ፱–፲።
፳፩ ᴼ ቅ.መ.መ. አለማዊነት።
ᴬ ዘፀአ. ፳ ፡ ፲፮፣
ማቴ. ፲፭ ፡ ፲፱–፳።
፳፪ ᴼ ሞዛያ ፯ ፡ ፳፱።
፳ᴱ ᴼ ሔለ. ፲፭ ፡ ፲፩–፲፭።
፳፬ ᴼ አልማ ፱ ፡ ፲፱።
ᴬ አልማ ፱ ፡ ፲፯፣
ት. እና ቃ. ፭ ፡ ፴ᴱ።
፳፭ ᴼ ሔለ. ᴱ ፡ ፳ᴱ።
፳፯ ᴼ ያዕቆ. ፪ ፡ ᴱᴱ።
ᴬ ኢሳ. ፭ ፡ ፳–፳፭።
፳፱ ᴼ አልማ ፭ ፡ ፶፭–ማ፯።

ምዕራፍ ፲

ምግባረ ብልሹ የሆኑት ዳብኛዎች ህዝቡ በኔፊ ላይ እንዲነሳሳ ፈለጉ—አብርሃም፣ ሙሴ፣ ዘሮስ፣ ዜኖቅ፣ ኤፅያስ፣ ኢሳይ ያስ፣ ኤርሚያስ፣ ሌሂ እና ኔፊ ሁሉም ስለ ክርስቶስ መሰከሩ—ኔፊ በመንፈስ ተነ ሳስቶ የዋናውን ዳኛ መገደል አስታወቀ። ከ፳፫–፳፩ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም አሁን እንዲህ ሆነ ኔፊ እነኚህን ቃላት በተናገረ ጊዜ፤ እነሆ ዳኞች የነበሩ፣ ደግሞም የጋድያንቶን የሚስጥር ቡድን አባላት የሆኑ ሰዎች ነበሩና፣ ተቆጥተውት ነበር፤ እናም ለህዝቡም እንዲህ በማለት በእርሱ ላይ ጮኹ፥ ይህ ሰው ለፈፀመው ወንጀል ይፈረድበት ዘንድ ለምን ይዛች ሁት አታመጡትም?

፪ ይህ ሰው ህዝቡን ሲሳደብ፣ እናም ህጋ ችንን ሲቃወም ለምን ዝም ብላችሁ ታዩታ ላችሁ፤ ለምንስ ትሰሙታላችሁ?

፫ እነሆም ኔፊ ስለህጋቸው ብልሹነት ለእ ነርሱ ተናግሮ ነበር፤ አዎን፣ ኔፊ ሊፃፉ የማ ይችሉ ብዙ ነገሮችን ተናግሯል፤ እናም የእ ግዚአብሔርን ትዕዛዛት የሚቃረን ምንም አልተናገረም ነበር።

፬ እናም ስለጨለማው ስራቸው [ሀ]በግልፅ ይናገር ስለነበር ዳኞቹም ተቆጥተው ነበር፤ ይሁን እንጂ ህዝቡ ስለፈሩ እናም ይጮሁ ብናል ብለው ስለፈሩ እርሱን ለመንካት አልደፈሩም ነበር።

፭ ስለዚህ በህዝቡ ላይ እንዲህ በማ ለት ጮኹ፥ ይህ ሰው እኛን እንዲሰድበን ለምን ፈቀዳችሁለት? እነሆም በዚህ ህዝብ ሁሉ ላይ እስከጥፋት ድረስ ይኮንናች ዋል፤ አዎን፣ እናም ደግሞ እነኚህ ታላ ላቆቹ ከተሞቻችን ከእኛ እንደሚወሰዱ፣ ስለዚህ እኛም በእነርሱ ቦታ እንደማይኖ ረን ተናግሯል።

፮ እናም እንግዲህ ይህ የማይቻል እንደ ሆነ እናውቃለን፣ እነሆም ኃያል ነን፣ እናም ከተሞቻችን ታላላቅ ናቸው፤ ስለዚህ ጠላ ቶቻችን በእኛ ላይ ስልጣን አይኖራቸውም።

፯ እናም እንዲህ ሆነ ህዝቡ በኔፊ ላይ በቁጣ እንዲነሳሳ አደረጉ፤ እናም በመካከላቸው ፀብ ቀሰቀሱ፤ ጥቂቶችም እንዲህ በማለት የሚጮኹ ነበሩ፥ ይህ ሰው መልካም ስለ ሆነ ተዉት፣ እናም እነዚህ እርሱ ያላቸው ነገሮች ንስሃ ካልገባን በእርግጥ ይሆናሉ፤

፰ አዎን እነሆ ለእኛ የመሰከረው ፍርድ በሙሉ በእኛ ላይ ይመጣል፤ ስለክፋታችን በትክክል መመስከሩን አውቀናልና። እናም እነሆ እነርሱም ብዙ ናቸው፤ እናም ክፋቶ ቻችንን [ሁ]እንደሚያውቃቸው ሁሉ የሚደር ሱብንን ሁሉንም ነገሮች ያውቃል፤

፱ አዎን እናም እነሆ፤ ነቢይ ባይሆን ኖሮ ስለእነዚህ ነገሮች መመስከር ባልቻለም ነበር።

፲ እናም እንዲህ ሆነ ኔፊን ለማጥፋት የፈ ለጉት ሰዎች፣ በፍርሃታቸው እጃቸውን በእርሱ ላይ እንዳያደርጉ ተገደው ነበር፤ ስለዚህ በጥቂቶች አይኖች ድገፋ በማግ ኘቱ የተቀሩት እንደሚፈሩ በተመለከተ ጊዜ በድጋሚ ለእነርሱ መናገርን ጀመረ።

፲፩ ስለዚህ እንዲህ በማለት ይበልጥ ለመ ናገር ተገፋፋ፥ እነሆ፣ ወንድሞቼ፣ [ሀ]የቀይ ባህር ውሃን በመምታት፣ እናም ለሁለት በመክፈል አባቶቻችን የሆኑትን እስራኤላ ውያንን በደረቁ መሬት እንዳሻገራቸው፣ እናም ግብፃውያን ወታደሮች ውሃው ተዘ ግቶባቸው ይውጣቸው ዘንድ ስልጣንን እግ ዚአብሔር ለዚያ ለአንድ ሰው፣ እንዲሁም ለሙሴ እንደሰጠ አላነበባችሁምን?

፲፪ እናም አሁን እነሆ፣ እግዚአብሔር ለዚህ ሰው እንደዚህ ዓይነት ስልጣን ከሰጠ፣ ንስሃ ካልገባችሁ በእናንተ ላይ ለፍርድ የሚመጣውን አውቅ ዘንድ ስልጣን አል ሰጠውም በማለት እርስ በእርሳችሁ ለምን ትጣላላችሁ?

፳ ፩ ሀ ፩ ኔፊ ፲፯፡ ፪–፫።
፳ ሀ ሔለ. ፯፡ ፳፱።
፲፩ ሀ ዘፀአ. ፲፡ ፲፯፤
፩ ኔፊ ፲፯፡ ፳፯፤
ሞዛያ ፯፡ ፲፱፤
ት. እና ቃ. ፳፡ ፪–፫፤
ሙሴ ፩፡ ፳፩።

፲፫ ነገር ግን እነሆ፣ ቃሌን ብቻ አይደለም
የካዳችሁት፣ ነገር ግን በአባቶቻችን የተነገ
ሩትን ቃላት በሙሉ ክዳችኋል፤ ደግሞም
ይህ ታላቅ ስልጣን በተሰጠው በሙሴ የተነ
ገሩትን ቃላት፣ አዎን ስለመሲሁ መምጣት
የተናገሯቸውም ቃላት ክዳችኋል።
፲፬ አዎን፣ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሚ
መጣ አልመሰከረምን? እናም የናስ እባብን
በምድረበዳው ውስጥ [ሀ]እንዳነሳ የሚመጣ
ውም እንዲሁ ይነሳል።
፲፭ እናም ብዙዎች እባቡን ተመልክተው
[ለ]በህይወት እንደኖሩ፣ በእምነት፣ በተዋ
ረደ መንፈስ በመሆን የእግዚአብሔርን ልጅ
ቢመለከቱ እስከዘለዓለማዊው ህይወት እን
ኳን [ሐ]ህያው እስከሚሆኑ ድረስም ይኖራሉ።
፲፮ እናም አሁን እነሆ፣ ስለእነዚህ ነገሮች
የመሰከረው ሙሴ ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን
ከእርሱ ዘመን ጀምሮ እስከ አብርሃም ዘመን
[መ]ቅዱሳን ነቢያትም ሁሉ ናቸው።
፲፯ አዎን፣ እናም እነሆ፣ [ሠ]አብርሃም ስለ
እርሱ መምጣት ተመልክቷልና፣ በስኬት
ተሞልቶ ነበር፤ እናም ተደስቶ ነበር።
፲፰ አዎን፣ እናም እነሆ እንዲህ እላች
ኋለሁ፣ ስለእነዚህ ነገሮች ያውቅ የነበ
ረው አብርሃም ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን
ከአብርሃም ዘመን በፊት በእግዚአብሔር
[ረ]ስርዓት የተጠሩ [ሰ]ብዙዎች ነበሩ፤ አዎን
በልጁም ስርዓት መሠረት እንኳን፤ እናም
ይህም ቤዛነትም እንኳን ለእነርሱ እንደሚ
መጣ፣ ከእርሱ መምጣት ከብዙ ሺህ ዓመ
ታት በፊት ለህዝቡ ይታይ ዘንድ ነው።
፲፱ እናም እንግዲህ ከአብርሃም ዘመን
ጀምሮ ስለእነዚህ ነገሮች ብዙ የመሰከሩ
ነቢያት መኖራቸውን እንድታውቁ እፈል
ጋለሁ፤ አዎን፣ እነሆ፣ ነቢዩ [ሸ]ዜኖስ በድፍ
ረት መስክሯል፤ ለዚህም ተገድሏልና።
፳ እናም እነሆ፣ ደግሞ [ቀ]ዜኖቅም፣ ደግሞ
ኤፅያስም፣ ደግሞ [በ]ኢሳይያስም፣ [ተ]ኤርምያ
ስም (ስለ [ቸ]ኢየሩሳሌም መጥፋት የተነበየው
ይኸው ነቢዩ ኤርምያስ) እናም አሁን እንደ
ኤርምያስ ቃል ኢየሩሳሌም እንደጠፋች
እናውቃለን። አቤቱ የእግዚአብሔር ልጅ
እንደትንቢቱ መሰረት ለምን አይመጣም?
፳፩ እናም እንግዲህ [ኀ]ኢየሩሳሌም እንደ
ጠፋች በዚህ ትከራከራላችሁን? የሴዴቅያስ
[ነ]ልጆች [ኘ]ከሙሌቅ በስተቀር ሁሉም አል
ተገደሉም ትላላችሁን? አዎን እናም የሴ
ዴቅያስ ዘሮች ከእኛ ጋር መሆናቸውንና፣
ከኢየሩሳሌም ምድር መባረራቸውን አል
ተመለከታችሁምን? ነገር ግን እነሆ፣ ይህ
ብቻም አይደለም—
፳፪ አባታችን ሌሂ ስለእነዚህ ነገሮች በመ
መስከሩ ከኢየሩሳሌም እንዲወጣ ተደር
ጓል። ኔፊም ደግሞ ስለእነዚህ ነገሮች መስ
ክሯል፣ እናም ደግሞ ከሞላ ጎደል አባቶቻ
ችን ሁሉ እስከዚህ ጊዜ ድረስ መስክረዋል፤
አዎን [ሰ]ስለክርስቶስ መምጣት መስክረዋል፤
የወደፊቱንም ጠብቀዋል፤ እናም ሊመጣ
ባለውም በእርሱም ቀን ተደስተዋል።
፳፫ እናም እነሆ፣ ክርስቶስ አምላክ ነው፣
እርሱም ከእነርሱ ጋር ነው፣ እራሱንም ገል
ፆላቸዋል፣ በእርሱም ድነዋል፤ እናም በሚ
መጣውም የተነሳ ለእርሱ ክብርን ሰጥተ
ውታል።

፲፬ [ሀ] ዘኁል. ፳፩፡፮–፱፣ ፪ ኔፊ ፳፭፡፳፣ አልማ ፴፫፡፲፱–፳፪። ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—የክርስቶስ ምሳሌዎች እና ምልክቶች።
፲፭ [ለ] ፩ ኔፊ ፲፯፡፵፩፣ አልማ ፴፯፡፵፩–፵፯፣ ፫ ኔፊ ፲፭፡፱።
[ሐ] ዮሐ. ፲፩፡፳፭።
፲፮ [መ] ያዕቆ. ፬፡፬–፭፣ ፯፡፲፩።
፲፯ [ሠ] ዘፍጥ. ፳፪፡፳–፲፰፣ ዮሐ. ፳፡፶፮።
፲፰ [ረ] ቅ.መ.መ. የመልከ ጼዴቅ ክህነት።
[ሰ] አልማ ፲፫፡፲፱፣ ት. እና ቃ. ፹፬፡፮–፲፮፣ ፻፴፮፡፴፯።
፲፱ [ሸ] አልማ ፴፬፡፮።
[ቀ] [በ] ፩ ኔፊ ፲፱፡፲፣ ፫ ኔፊ ፲፡፲–፲፮።
[ተ] ቅ.መ.መ. ቅዱሳት መጻህፍት—የጠፉ ቅዱሣት መጻህፍት።
[ቸ] ኢሳ. ፶፫።
[ኀ] ፩ ኔፊ ፭፡፲፫፣ ፯፡፲፱።
[ነ] ኤር. ፳፯፡፲፣ ፲፰፣ ፩ ኔፊ ፭፡፱።
[ኘ] ፪ ነገሥ. ፳፭፡፯፣ ኤር. ፴፱፡፯፣ ፶፪፡፲።
[ሐ] ሕዝ. ፲፯፡፳፪–፳፫፣ ሔሌ. ፭፡፲።
[ቀ] [ሠ] ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—ስለኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ እና ሞት ትንቢቶች።

፯፬ እናም እንግዲህ፣ እነዚህን ነገሮች በማወቃችሁ፣ እናም ካልዋሻችሁ በቀር ልትክዱአቸው አትችሉም፤ ስለዚህ በዚህም ኃጢያትን ሰርታችኋል፤ ምክንያቱም ምንም እንኳን ብዙ ምስክሮችን የተቀበላችሁ ቢሆንም አዎን እውነት ለመሆናቸው ምስክር እንዲሆኑ በሰማይ እንዲሁም በምድር ያሉትን [ሀ]ነገሮች በሙሉ ከተቀበላችሁ በኋል፣ እነዚህን ነገሮች በሙሉ ስላልተቀበላችሁ ነው።

፯፭ ነገር ግን እነሆ፣ እውነትን አልተቀበላችሁም እናም በቅዱሱ አምላካችሁም ላይ [ለ]አምፃችኋል፤ እናም በዚህ ጊዜም እንኳን ቢሆን በሰማይ ንፁህ ያልሆነ ነገር ሊመጣበት በማይችለው ሥፍራ ለራሳችሁ የማይበላሽውን [ሐ]ሀብት በማስቀመጥ ፈንታ [መ]በፍርድ ቀን የሚሆን ቁጣን በራሳችሁ ላይ ታከማቻላችሁ።

፯፮ አዎን፣ በዚህ ጊዜም እንኳን በመግደላችሁ፤ እናም [ሠ]ዝሙት በመፈፀማችሁ እንዲሁም በክፋታችሁ ለዘለዓለማዊው ጥፋት በስላችኋል፤ አዎን፣ እናም ንስሃ ካልገባችሁ በቅርቡ በራሳችሁ ላይ ይመጣል።

፯፯ አዎን፣ እነሆ ይህም አሁን በደጃችሁ ላይ ነው፤ አዎን፣ ወደ ፍርድ ወንበሩ ሂዱና ፈልጉ፤ እናም እነሆ የእናንተ ዳኛ ተገድሎና፣ [ረ]በደሙም ውስጥ ወድቋል፤ በፍርድ ወንበሩ ላይ ለመቀመጥ በፈለገው [ሰ]በወንድሙም ተገድሏል።

፯፰ እናም እነሆ ሁለቱም [ሸ]ደራሲ ጋድያንቶንና የሰዎችን ነፍስ ለማጥፋት የሚፈልገው የክፉው የሆነው የሚስጥራዊው ቡድን አባላት ናቸው።

ምዕራፍ ፱

መልዕክተኞች ዋናው ዳኛ በፍርድ ወንበሩ ላይ ሞቶ አገኙት—እነርሱም ታሰሩ፣ በኋላም ተለቀቁ—በመንፈስ በመነሳሳት ኔፊ ሴአንቱም ገዳይ መሆኑን አሳወቀ—ኔፊ በጥቂቶች ነቢይ ተብሎ ተቀባይነትን አገኘ። ከ፳፫–፳፭ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እነሆ እንዲህ ሆነ ኔፊ እነዚህን ቃላት በተናገረ ጊዜ ከእነርሱ ጋር የነበሩ አንዳንድ ሰዎች ወደ ፍርድ ወንበሩ ሮጡ፤ አዎን አምስት ነበሩ፤ እናም በተጓዙ ጊዜ በመካከላቸው እንዲህ ሲሉ ተናገሩ፥

፪ እነሆ፣ አሁን ይህ ሰው በእርግጥ ነቢይ መሆኑን፣ እናም እንደዚህ ያሉ ድንቅ ነገሮችን እንዲተነብይ እግዚአብሔር እንዳዘዘው በእርግጥ እናውቃለን። እነሆ፣ እርሱ አዘታል ብለን አናምንም፤ አዎን፣ ነቢይ ነው ብለንም አናምንም፤ ይሁን እንጂ፣ ስለዋናው ዳኛ ይሞታል በማለት የተናገረው ይህ ነገር እውነት ከሆነ ሌሎች የሚናገራቸው ቃላት እውነት ናቸው ብለን እና ምናለን።

፫ እናም እንዲህ ሆነ በኃይል ሮጡና፣ ወደ ፍርድ ወንበሩ መጡ፤ እናም እነሆ፣ ዋናው ዳኛ በመሬት ላይ ወድቋልና [ተ]ከነደሙም ተኝቷል።

፬ እናም አሁን እነሆ፣ ይህንን በተመለከቱ ጊዜ እጅግ ተገርመው ነበር፤ ስለዚህ በመሬት ላይ ወደቁ፤ ምክንያቱም ኔፊ ስለ ዋናው ዳኛ የተናገራቸውን ቃላት አላመኑም ነበር።

፭ ነገር ግን አሁን፣ በተመለከቱ ጊዜ አመኑ፣ እናም ኔፊ የተናገረው ቅጣት ሁሉ በህዝቡ ላይ ይመጣል የሚል ፍርሃት በእነርሱ ላይ ሆነ፤ ስለዚህ ተንቀጠቀጡ፣ እናም በመሬት ላይ ወደቁ።

፮ እንግዲህ፣ ዳኛው በተገደለበት ጊዜ ወዲያው—ምስጢራዊ ልብስ በለበሰው ወንድሙ ተወግቶ፣ እናም እርሱም ሸሽና፣ አገልጋዮቹ ሮጡ፣ እናም ለህዝቡ በመካከ

፯፬ *ሀ* አልማ ፴፡ ፵፬፤ ሙሴ ፮፡ ፳፫።
፯፭ *ሀ* ሞዛያ ፪፡ ፴፯–፴፯፤ ፫፡ ፲፪።
ለ ሔለ. ፭፡ ፳፣
፫ ኔፊ ፲፫፡ ፲፱–፳፭።
ሐ ት.እና ቃ. ፲፡ ፳–፳፫፤ ፲፳፭፡ ፳፫–፳፭።
፯፭ *ሀ* ቅ.መ.መ. ዝሙት መፈጸም።
፯፮ *ሀ* ሔለ. ፱፡ ፫፣ ፲፭።
ለ ሔለ. ፱፡ ፮፣ ፳፮–፴፳።
፯፯ *ሀ* ሔለ. ፮፡ ፳፮–፴።
፱ ፫ *ሀ* ሔለ. ፳፡ ፳፮።

ላቸው ግድያ እንደነበረ ድምፃቸውን ከፍ
በማድረግ ተናገሩ፤
፲ እናም እነሆ ህዝቡ በአንድነት በፍርድ
ወንበሩ ስፍራ ራሳቸውን ሰበሰቡ—እናም
እነሆ በመገረም በመሬት ላይ የወደቁትን
አምስት ሰዎች ተመለከቱ።
፲፩ እናም እንግዲህ እነሆ፣ [a]በኔፊ የአት
ክልት ስፍራ በአንድነት ስለተሰበሰቡት
ሰዎች ህዝቡ ምንም አያውቅም ነበር፤ ስለ
ዚህ እርስ በርሳቸውም እንዲህ ተባባሉ፥
እነዚህ ሰዎች ዳኛውን የገደሉት ናቸው፣
እናም ከእኛ እንዳይሸሹ እግዚአብሔር
መታቸዋል።
፲፪ እናም እንዲህ ሆነ ያዙአቸውና፣ አሰ
ሩአቸው፣ ወደ ወህኒ ቤትም ጣሉአቸው።
እናም ዳኛው ስለመገደሉና፣ ገዳዩ ተወሰ
ደና ወደ ወህኒ ቤት እንደተጣሉ ዜናው በሁ
ሉም ስፍራ ተሰራጨ።
፲፫ እናም እንዲህ ሆነ በሚቀጥለው ቀን
በተገደለው በዋናው ዳኛ ቀብር ላይ ለማ
ዘን፣ እናም [b]ለመፆም ህዝቡ በአንድ ላይ
እራሱን ሰበሰበ።
፲፬ እናም እነዚህ በኔፊ የአትክልት ስፍራ
የነበሩት፣ እናም ቃሉን የሰሙት ዳኞች
ደግሞም በቀብሩ ላይ በአንድነት ተሰብ
ሰበው ነበር።
፲፭ እናም እንዲህ ሆነ በህዝቡ መካ
ከል እንዲህ በማለት ጠየቁ፥ ዋናው ዳኛ
መሞቱን በተመለከተ ለመጠየቅ የተላኩት
አምስቱ የት አሉ? እናም መለሱና እንዲህ
አሉ፥ ልከናችኋል ስላላችኋቸው ስለእነዚህ
አምስቱ ምንም አናውቅም፤ ነገር ግን ገዳ
ዮች የሆኑ ወደ ወህኒ ቤት የጣልናቸው አም
ስት አሉ።
፲፮ እናም እንዲህ ሆነ ዳኞቹ እነዚህ ወደ
እነርሱ እንዲመጡ ፈለጉ፤ እናም አመ
ጡዋቸውና፣ እነርሱም የተላኩት አምስቱ
እንደነበሩ ተመለከቱ፤ እናም እነሆ ጉዳ
ዩን በተመለከተ ለማወቅ ዳኞቹ ጠየቁአቸ
ውና፣ ያደረጉትን በሙሉ እንዲህ በማለት
ነገሩአቸው፥
፲፯ ሮጥን፣ እናም ወደ ፍርድ ወንበሩ
መጣንና፣ ኔፊ እንደመሰከራቸው ሁሉ
ንም ነገሮች ስንመለከት፣ መሬት እስከም
ንወድቅም ድረስ ተገረምን፤ እናም ከመገ
ረማችን በተመለስን ጊዜ፣ እነሆ ወደ ወህኒ
ቤት ጣሉን።
፲፰ እንግዲህ፣ የዚህን ሰውዬ ግድያ በተ
መለከተ ማን እንዳደረገው አናውቅም፤
እናም እስከዚህ ብቻ ነው የምናውቀው፤
ሮጥንና እንደ ፍላጎታችሁ መጣን፣ እናም
እንደ ኔፊ ቃላት መሞቱን ተመለከትን።
፲፱ እናም አሁን እንዲህ ሆነ ዳኞቹ ጉዳ
ዩን ለህዝቡ ገለፁና፣ በኔፊም ላይ እንዲህ
ሲሉ ጮኹ፥ እነሆ ይህ ኔፊ ዳኛውን ለመግ
ደል ከአንድ ሰው ጋር ተስማምቶ ይሆናል፣
ከዚያም እኛን ወደ እርሱ እምነት ለመለወጥ
እራሱን ታላቅ ሰው ለማድረግ፣ በእግዚ
አብሔር የተመረጠና ነቢይ ያደርግ ዘንድ
ይህን ለእኛ ይናገራል።
፲፯ እናም እንግዲህ እነሆ፣ ይህንን ሰው
እናገኘዋለን፣ ስህተቱንም ይናዘዛል፣ እናም
የዚህን ዳኛ እውነተኛ ገዳይ እንድናውቀው
ያደርገናል።
፲፰ እናም እንዲህ ሆነ በቀብሩ ቀን
አምስቱ ነፃ ወጡ። ይሁን እንጂ፣ በኔፊ ላይ
በሚናገሩት ቃላት ዳኞቹን ገሰፁአቸው፣
እናም ዳኞቹም ዝም እንዲሉ እስከሚያደ
ርጉአቸው ድረስ አንድ በአንድ ተከራክ
ሯዋቸው።
፲፱ ይሁን እንጂ፣ ኔፊ እንዲወሰድና፣
እንዲታሰር፣ እናም በህዝቡ ፊት እንዲ
መጣ አደረጉትና፣ እርሱን በሞት እንዲ
ቀጣ ለመክሰስ፣ እንዲቃረናቸው በተለያየ
መንገድ ይጠይቁት ጀመር—
፳ እንዲህም አሉት፥ አንተ ከሌሎች ተባ
ባሪ ነህ፤ ግድያውንስ የፈፀመው ይህ ሰው
ማን ነው? አሁን ንገረንና ጥፋትህን ተቀ
በል፤ እንዲህም አሉት፤ እነሆ ገንዘብ ይኸ
ውና፤ እናም ደግሞ የምትነግረንና፣ ከእርሱ
ጋር የተስማማህበትን የምታሳውቀን ከሆነ
ህይወትህን እናተርፍልሃለን።

[a] ሆ ሐለ. ፲፡፲፡ [b] ሆ ቅ.መ.መ. ጾም፣ መጾም።

፳፩ ነገር ግን ኔፊ እንዲህ አላቸው፥ እና
ንተ ᵇሞኞች ሆይ በልባችሁም ያልተገረዛ
ችሁ፤ እውሮች እናም ᵃአንገተ ደንዳና የሆ
ናችሁ፣ ጌታ አምላካችሁ በዚህ በኃጢያት
መንገዳችሁ እንድትሄዱ ለምን ያህል ጊዜ
እንደሚፈቅድላችሁ ታውቃላችሁን?
፳፪ አቤቱ፣ ንስሃ ካልገባችሁ በዚህ ጊዜ
በሚጠብቃችሁ ታላቅ ጥፋት የተነሳ በሰቆቃ
መጮህ እንዲሁም ᵇማዘን አለባችሁ።
፳፫ እነሆ ዋና ዳኛችን የሆነውን ሲኤዞራ
ምን ከሚገድለው ሰውዬ ጋር ተስማምቻለሁ
ብላችኋል። ነገር ግን እነሆ፣ እንዲህ እላች
ኋለሁ፥ ይህ የሆነበት መንስኤ ስለዚህ ነገር
ታውቁ ዘንድ ስለመሰከርኩ ነው፤ አዎን፣
በመካከላችሁ ያለውን ክፋትና እርኩሰት
የማወቁ ለምስክር እንዲሆንላችሁ ነው።
፳፬ እናም ይህንን በማድረጌ ይህንን ነገር
እንዲፈጽም ከአንድ ሰው ጋር እንደተስማ
ማሁ ተናገራችሁ፤ አዎን፣ ይህን ምልክት
ስላሳየኋችሁ በእኔ ተቆጣችሁ፣ እናም ህይ
ወቴን ለማጥፋት ፈለጋችሁ።
፳፭ እናም አሁን እነሆ ሌላ ምልክት አሳ
ያችኋለሁ፣ እናም በዚህ ነገር እኔን ለማጥ
ፋት እንደምትፈልጉም አያለሁ።
፳፮ እነሆ እንዲህ እላችኋለሁ፥
ᵇየሲኤዞራም ወንድም ወደሆነው ወደ ሴአን
ቱም ቤት ሂዱ፤ እናም እንዲህ በሉት—
፳፯ ስለዚህ ህዝብ ብዙ ክፉ የሚተነብ
የው አስመሳዩ ነቢይ፣ ኔፊ፣ ወንድምህን
ሲኤዞራምን በመግደል ከአንተ ጋር ተስ
ማምቷልን?
፳፰ እናም እነሆ እርሱ ግን አይደለም ይላ
ችኋል።
፳፱ እናም እናንተ እንዲህ ትሉታላችሁ፥
ወንድምህን ገድለኸዋልን?
፴ እናም እርሱ በፍርሃት ይቆማል፣ ምን
ማለት እንዳለበትም አያውቅም። እናም
እነሆ ይክድላችኋል፤ የተገረመ ለመምሰ
ልም ይሞክራል፤ ይሁን እንጂ በዚህ ነገር
ተጠያቂ አለሆኑንም ለእናንተ ይናገራል።
፴፩ ነገር ግን እነሆ ትመረምሩታላችሁ፤
እናም በልብሱም ጫፍ ላይ ደም ታገኛላ
ችሁ።
፴፪ እናም ይህን በተመለከታችሁ ጊዜ
እንዲህ ትላላችሁ፥ ይህ ደም ከየት መጣ?
የወንድምህ ደም መሆኑንስ አናውቅምን?
፴፫ እናም ከዚያን በኋላ ይንቀጠቀጣል፣
እናም ሞት በላዩ ላይ የመጣ ይመስል ይገ
ረጣል።
፴፬ እናም እንዲህ ትሉታላችሁ፥ በፍርሃ
ትህና ፊትህ በመገርጣቱ፣ እነሆ፣ ጥፋተኛ
መሆንህን እናውቃለን።
፴፭ እናም ታላቅ ፍርሃት በላዩ ላይ ይመ
ጣል፤ እናም ለእናንተ ይናዘዝላችኋል፣
ይህንን ግድያ መፈፀሙንም ከእንግዲህ
አይክድም።
፴፮ እናም ከዚያ በኋላ በእግዚአብሔር
ከተሰጠኝ ኃይል በስተቀር ስለጉዳዩ እኔ
ኔፊ ምንም አላውቅም በማለት ይነግራች
ኋል። እና ከዚያም እኔ ታማኝ ሰው መሆኔ
ንና፣ ከእግዚአብሔር ወደ እናንተ የተላኩ
መሆኔን ታውቃላችሁ።
፴፯ እናም እንዲህ ሆነ ሄዱና፣ ኔፊ እን
ደተናገራቸው አደረጉ። እናም እነሆ እርሱ
የተናገራቸው ቃላት እውነት ነበሩ፤ በቃ
ላቱ መሰረትም ካደ፤ በቃላት መሰረትም
ተናዘዘ።
፴፰ እናም እርሱም ራሱ በእውነት ገዳይ
መሆኑ ተረጋገጠ፤ ስለዚህ አምስቱ እናም
ደግሞም ኔፊ ተለቀቁ።
፴፱ እናም የኔፊን ቃላት ያመኑ ጥቂት
ኔፋውያን ነበሩ፤ እናም ጥቂቶች አምስቱ
በወህኒ ቤት በነበሩበት ወቅት በመለወጣ
ቸው በእነርሱ ምስክርነት ያመኑ ነበሩ።
፴ እናም እንግዲህ ኔፊ ነቢይ ነበር ብለው
የተናገሩ በህዝቡ መካከል ጥቂት ነበሩ።
፴፩ እናም ሌሎችም እንዲህ ሲሉ የተና
ገሩ ነበሩ፥ እነሆ እርሱ አምላክ ነው፤ አም
ላክ ባይሆን ኖሮ ሁሉንም ነገሮች ሊያውቃ
ቸው አይቻለውም ነበር። እነሆም፣ የልባ

ᵃ፳፩ ሆ የሐዋ. ፯፡፶፩።
ᵇ ቅ.መ.መ. አመጽ።
ᵃ፳፪ ሆ ሞዛያ ፯፡፳፬።
ᵇ፳፮ ሆ ሔለ. ፰፡፳፯።

ችንን ሀሳብ ነግሮናልና ደግሞ ነገሮችንም ነግሮናል፤ እናም የዋናው ዳኛችን እውነተኛ የሆነውንም ገዳይ እንኳን እንድናውቀው አድርጓል።

ምዕራፍ ፲

ጌታ ለኔፊ የማሰር ስልጣንን ሰጠው—በመሬትና በሰማይ እንዲያስር እናም እንዲፈታ ስልጣንን ሰጠው—ሰዎች ንስሃ እንዲገቡ አለበለዚያም እንዲጠፉ አዘዘ—መንፈስ ከብዙ ህዝብ ወደ ብዙ ህዝብ ወሰደው። ከ፳፩–፳ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ በህዝቡ መካከል መከፋፈል ተፈጠረ፤ ስለዚህ ወዲህና ወዲያ ተከፋፈሉ እናም ኔፊ በመካከላቸው ቆሞ ሳለ ብቻውን ጥለውት በተለያየ አቅጣጫ ሄዱ።

፪ እናም እንዲህ ሆነ ኔፊ ጌታ ያሳየውን ነገሮች በልቡ ᵐእያሰላሰለ ወደ ራሱ ቤት መንገዱን አቀና።

፫ እናም እንዲህ ሆነ በሚያሰላስልበት ወቅት—በኔፊ ህዝብ የጨለማ ስራ፣ እንዲሁም ግድያና፣ ዝርፊያቸው፣ እንዲሁም በሁሉም ዓይነት ክፋታቸው እጅግ በማዘኑ—እናም እንዲህ ሆነ በልቡ በሚያሰላስልበት ወቅት፣ እነሆ፣ ድምፅ እንዲህ ሲል ወደ እርሱ መጣ፥

፬ ኔፊ ባደረግሃቸው ነገሮች አንተ የተባረክህ ነህ፤ ምክንያቱም ለዚህ ህዝብ የሰጠሁህን ቃል ᵐበፅኑነት እንዴት እንዳወጅክ አይቻለሁና። እናም አልፈራሃቸውም፣ ᵃለህ ይወትህም አልሰሰትህም፤ ነገር ግን የእኔን ᵐፈቃድና ትዕዛዛቴን ለመጠበቅ ይህን አድርገሃልና።

፭ እናም አሁን በፅኑነት ይህንን በማድረግህ፣ እነሆ ለዘለዓለም እባርክሃለሁ፤ እናም በቃልህና በስራህ፣ በእምነትና በተግባርህም ብርቱ አደርግሃለሁ፤ አዎን ከፈቃዴ የሚቃረን ነገር ᵐስለማትጠይቀኝ ᵃሁሉም ነገሮች ᵐእንደቃልህ ይሆኑልሃል።

፮ እነሆ፣ አንተ ኔፊ ነህ፣ እኔም እግዚአብሔር ነኝ። እነሆ፣ በመላዕክቶቼ ፊት፣ በዚህ ህዝብ ላይ ስልጣን እንደሚኖርህና፣ እንደ ህዝቡ ክፋት ምድርን ᵐበረሃብና፣ በቸነፈር፣ እናም በጥፋት፣ ለመምታት እንደምትችል እገልፅልሃለሁ።

፯ እነሆ፣ በምድር የምታስረው ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ እናም በምድርም የምትፈታው ሁሉ በሰማይ ᵐየተፈታ ይሆናል፤ እናም እንደዚህ በዚህ ህዝብ መካከልም ስልጣን ይኖርሃል።

፰ እናም ይህን ቤተመቅደስ ሁለት ቦታ ትከፈል የምትለው ከሆነ እንዲሁ ይሆናል።

፱ እናም ይህንን ᵐተራራ ውደቅና ሜዳ ሁን ብትለው እንዲሁ ይሆናል።

፲ እናም እነሆ፣ እግዚአብሔር ይህን ህዝብ ይመታዋል የምትል ከሆነ እንዲሁ ይሆናል።

፲፩ እናም አሁን እነሆ፣ እንድትሄድና ሁሉን የሚገዛው ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ አለ ብለህ ለዚህ ህዝብ እንድታውጅ አዝዘለሁ፥ ንስሃ ካልገባችሁ ᵐእስክትጠፉ ድረስ ትመታላችሁ።

፲፪ እናም እነሆ አሁን እንዲህ ሆነ ጌታ እነዚህን ቃላት ለኔፊ በተናገረ ጊዜ፣ ኔፊ ቆመ፣ እናም ወደ ቤቱም አልሄደም፣ ነገር ግን በምድሪቱ ገፅ ላይ ተበታትነው ወደ ነበሩት ሰዎች ተመለሰ፤ እናም ንስሃ ካልገቡ መጥፋታቸውን በተመለከተ የእግዚአብሔርን ቃል ማወጅ ጀመረ።

፲፫ እንግዲህ እነሆ፣ ስለዋናው ዳኛ ሞት ኔፊ ታላቁን አስደናቂ ነገር የተናገረ ቢሆንም ልባቸውን አጠጥረው ነበር፣ እናም የጌታን ቃላት አላዳመጡም።

፲ ፪ *ሀ* ቅ.መ.መ. ማስላሰል።
፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. ትጋት።
ለ ቅ.መ.መ. መስዋዕት።
ሐ ፣ ኔፊ ፲፩፡ ፲፩።
፭ *ሀ* ፪ ኔፊ ፡ ፡ ፣
ት. እና ቃ. ፣ ፡ ።
ለ ፣ ኔፊ ፲፰፡ ፣
ት. እና ቃ. ፡ ፣ ፡ ።
ሐ ኢኖስ ፩፡ ፲፪።
፯ *ሀ* ሔለ. ፲፩፡ ፡ ።
፯ *ሀ* ማቴ. ፲፯፡ ፣
ቅ.መ.መ. ማተም፣
ማስተሳሰር።
፱ *ሀ* ማቴ. ፲፯፡ ፣
ያዕቆ. ፡ ፣
ሞር. ፡ ፣
ኤተር ፲፪፡ ።
፲፩ *ሀ* ሔለ. ፡ ።

፲፩ ስለዚህ ኔፊ የጌታን ቃል እንዲህ በማ
ለት አወጀላቸው፡ ንስሃ ካልገባችሁ ይላል
ጌታ፣ እስክትጠፉም ድረስ ትመታላችሁ።
፲፪ እናም እንዲህ ሆነ ኔፊ ቃሉን በተናገረ
ጊዜ፣ እነሆ፣ ልባቸውን በማጠጠር ቀጠሉ፣
እናም ቃሉንም አላዳመጡትም ነበር፤ ስለ
ዚህ ሰደቡትና፣ ወደ ወህኒ ቤት ይጥሉትም
ዘንድ በእጃቸው ሊይዙት ፈለጉ።
፲፫ ነገር ግን እነሆ፣ የእግዚአብሔር ኃይል
ከእርሱ ጋር ነበር፤ እናም እርሱን ይዘው
ወህኒ ቤት ሊጥሉት አልቻሉም ነበር፣ ምክ
ንያቱም በመንፈስ ተወሰደ፣ እናም ከመካ
ከላቸውም ተወስዷል።
፲፬ እናም እንዲህ ሆነ ለሁሉም እስከሚ
ሰብክ ድረስ፣ ወይም በህዝቡ ሁሉ መካ
ከል እስከሚልከው ድረስ፣ የእግዚአብሔ
ርን ቃል በማወጅ፣ እንደዚህ ከህዝብ ወደ
ህዝብ በመንፈስ ይሄድ ነበር።
፲፭ እናም እንዲህ ሆነ ቃሉን አላዳመጡ
ትም ነበር፤ እናም ፀብ ተጀመረ፣ ስለዚህ
በመካከላቸው መከፋፈል ሆነና እርስ በእር
ሳቸው በጎራዴ መገዳደል ጀመሩ።
፲፮ እናም በኔፊ ህዝብ ላይ የመሣፍንቱ ሰባ
አንደኛ የንግስ ዘመን በዚሁ ተፈፀመ።

ምዕራፍ ፲፯

*ኔፊ ጌታ ጦርነታቸውን በረሃብ እንዲለ
ውጠው ለመነ—ብዙ ሰዎች ጠፉ—ንስሃ
ገቡ፤ እናም ኔፊ ዝናብ እንዲያመጣ ጌታን
በጥብቅ ለመነው—ኔፊ እና ሌሂ ብዙ ራዕ
ዮችን ተቀበሉ—የጋድያንቶን ዘራፊዎች
በምድሪቱ ላይ ተቋቋሙ። ከ፳–፳ ም.ዓ.
ገደማ።*

፩ እናም እንግዲህ እንዲህ ሆነ በመሣ
ፍንቱ ሰባ ሁለተኛ ዓመት የንግስና ዘመን
ፀቡ ተስፋፋ፤ ስለሆነም በኔፊ ሰዎች ሁሉ
መካከል በምድሪቱ ላይ በሙሉ ጦርነቶች
ነበሩ።
፪ እናም ይህንን የጥፋትና የተንኮል ስራ
ያከናውኑ የነበሩት እነዚህ ᵛሚስጥራዊ የሆ
ኑት የሌቦች ቡድን ነበሩ። እናም ጦርነቱ
በዚሁ ዓመት ሁሉ ቆይቷል፤ እናም እስከ
ሰባ ሶስተኛው ዓመትም ቆይቷል።
፫ እናም እንዲህ ሆነ በዚሁ ዓመት ኔፊ
እንዲህ በማለት ወደጌታ ጮኸ፡
፬ አቤቱ ጌታ፣ እነዚህ ሰዎች በጎራዴ እን
ዲጠፉ አትፍቀድ፤ ነገር ግን ጌታዬ ሆይ፣
ጌታ አምላካቸውን እንዲያስታውሱ ለማነ
ሳሳት በምድሪቱ ᵛረሃብ እንዲኖር አድርግ፤
እናም ምናልባት ንስሃ ይገባሉና፣ ወደ አንተ
ይመለሳሉ።
፭ እናም በኔፊም ቃል መሰረት ተከናወነ።
እናም በኔፊ ሰዎች መካከልም በሙሉ፣
በምድሪቱ ላይ ረሃብ ሆነ። እናም በሰባ አራ
ተኛው ዓመትም ረሃቡ ቀጠለና፣ የጥፋት
ስራው በጎራዴ መሆኑ ቆመ፣ ነገር ግን በረ
ሃብ ኃይለኛ ሆነ።
፮ እናም ይህ የጥፋትም ስራ ደግሞ በሰባ
አምስተኛው ዓመት ቀጠለ። ምድሪቱም
በመመታትዋ ደረቅ ነበረች፣ በእህል ወቅ
ትም እህልን አልሰጠችም፤ እናም ምድ
ሪቱ በሙሉ ተመታች፤ በላማናውያን እን
ዲሁም በኔፋውያን መካከልም፣ በምድሪቱ
በይበልጥ ክፉ በሆኑት አካባቢ በሺህ የሚቆ
ጠሩት በመመታታቸው ሞቱ።
፯ እናም እንዲህ ሆነ በረሃብ ሊጠፉ መቃ
ረባቸውን ሰዎቹ ተመለከቱና ጌታ አምላካ
ቸውን ᵛማስታወስ ጀመሩ፤ እናም የኔፊንም
ቃል ማስታወስ ጀመሩ።
፰ እናም ሰዎቹ ከዋና ዳኞቻቸው እንዲ
ሁም ከመሪዎቻቸው ጋር ኔፊን እንዲህ እን
ዲሉ መማፀን ጀመሩ፡ እነሆ፣ አንተ የእ
ግዚአብሔር ሰው መሆንህን እናውቃለን፣
እናም ስለዚህ ስለጥፋታችን የተናገርካቸው
ᵛቃላት ሁሉ እንዳይፈፀሙ ዘንድ ይህንን
ረሃብ ከእኛ እንዲመልሰው ወደ ጌታ አም
ላካችን ጩህ።
፱ እናም እንዲህ ሆነ ዳኞቹም በተፈለ
ገው ቃላት መሰረት ኔፊን ተናገሩት። እናም

፲፭ ᵛᵛ ሔለ. ፮፡፲፰–፳፡ ᵛ ᵛ ነገሥ. ፲፯፡፩፣ ᵛ ᵛ ሔለ. ፲፣ ፮። ᵛ ᵛ ሔለ. ፲፪፡፲። ᵛᵛ ᵛ ᵛ ሔለ. ፲፡፲፩–፲፡

እንዲህ ሆነ ሰዎቹ ንስሃ መግባታቸውንና፣ ትቢያንም ለብሰው እራሳቸውን ዝቅ ማድ ረጋቸውን በተመለከተ ጊዜ በድጋሚ ወደ ጌታ እንዲህ በማለት ጮኹ፡

፲ አቤቱ ጌታ፣ እነሆ እነዚህ ሰዎች ንስሃ ገብተዋል፤ እናም ከመካከላቸው የጋድያን ቶን ቡድን የሆኑትን ጨርሰው እስከሚጠፉ አባረዋቸዋል፤ እናም ሚስጥራዊ አሴራቸ ውንም በምድር ቀብረዋል።

፲፩ እንግዲህ፣ ጌታ ሆይ፣ በዚህ በትሁት ነታቸው ምክንያት ቁጣህን ትመልሳለህን፣ እናም አንተ ባጠፋሃቸው ኃጢአተኛ ሰዎች ቁጣህ በዚህ ያብቃ።

፲፪ ጌታ ሆይ ቁጣህን አዎን፣ ኃያሉ ቁጣ ህን ትመልሳለህን፤ እናም ይህ ረሃብ በዚህ ምድር እንዲጠፋም አድርግ።

፲፫ ጌታ ሆይ፣ እኔንም አድምጥ፤ እናም እንደቃሌም ይሆን ዘንድ አድርግ፤ እናም ምድርም ፍሬን እንድታፈራና በእህል ወቅት እህል እንድታፈራ በምድር ገፅ ᐟዝና ብን አዝንብ።

፲፬ ጌታ ሆይ፣ የጎራዴው ቁጣም ይቆም ዘንድ ረሃብ ይሁን ባልኩ ጊዜም ᐟቃሌን አደመጥህ፤ እና በዚህ ጊዜም እንኳን ቃላቶ ቼን እንደምታደምጥ አውቃለሁ፣ ምክንያ ቱም እነዚህ ሰዎች ንስሃ ከገቡ አድናቸዋ ለሁ በማለት ተናግረሃልና።

፲፭ አዎን፣ ጌታ ሆይ፣ በረሃቡና፣ በቸነ ፈሩ፣ እናም በእነርሱ ላይ በመጣው ጥፋ ትም የተነሳ ንስሃ እንደገቡ ተመልክተ ሃል።

፲፮ እናም እንግዲህ ጌታ ሆይ፣ ቁጣህን ትመልሳለህ፣ እናም እንደሚያገለግሉህ እንደገና ትሞክራቸዋለህን? እንደዚህ ካደ ረግህ፣ ጌታ ሆይ በተናገርከው ቃል መሰረት ልትባርካቸው ትችላለህ።

፲፯ እናም እንዲህ ሆነ በሰባ ስድስተኛው ዓመት ጌታ ቁጣውን ከህዝቡ መለሰና፣ በምድር ላይም ᐟዝናብ እንዲዘንብ አደረገ፤ ስለዚህ ይህም በምድር በፍሬዋ ወቅት ፍሬ ሰጣት። እናም እንዲህ ሆነ በእህል ወቅትም እህል እንዲሆን አደረገ።

፲፰ እናም እነሆ፣ ህዝቡ ተደሰተና፣ እግ ዚአብሔርን አከበረ፤ የምድሪቱም ገፅ በሙሉ በደስታ ተሞላ፤ እናም ኔፊን ለማ ጥፋት ሙከራ አላደረጉም፤ ነገር ግን ᐟእን ደታላቅ ነቢይና፣ የእግዚአብሔር ሰው፣ ታላቅ ኃይልና ስልጣን ከእግዚአብሔር የተሰጠው በማድረግ አከበሩት።

፲፱ እናም እነሆ፣ ሌሂ የፅድቅ ነገሮችን በተመለከተ ወንድሙም ከእርሱ ᐟያነሰ አልነበረም።

፳ እናም እንዲህ ሆነ የኔፊ ሰዎች በምድ ሪቱ ላይ እንደገና መበልፀግ ጀመሩ፣ እናም ከሰሜን በኩልና፣ ከደቡብ ከባህሩ በስተ ምዕራብ እስከባህሩ በስተምስራቅ ምድሪ ቱን በሙሉ እስከሚሸፍኑ ድረስ መብዛት እንዲሁም መሰራጨት ጀመሩ፣ የፈራረሱ ስፍራዎችንም መገንባት ጀመሩ።

፳፩ እናም እንዲህ ሆነ ሰባ ስድስተኛው ዓመት በሰላም ተፈፀመ። እናም ሰባ ሰባ ተኛው ዓመትም በሰላም ተጀመረ፤ ᐟቤተ ክርስቲያኗም በምድር ገፅ ሁሉ ላይ ተሰራ ጨች፤ የኔፋውያን እንዲሁም የላማናውያን ሰዎች በአብዛኛው የቤተክርስቲያኗ አባላት ነበሩ፣ እናም በምድራቸውም እጅግ ታላቅ ሰላም ነበራቸው፤ እንደዚህም ሰባ ሰባተ ኛው ዓመት ተፈፀመ።

፳፪ እናም ደግሞ በሰባ ስምንተኛው ዓመት በነቢያት በሚወጡ የእምነት ነጥቦ ችን በተመለከተ ከነበረው ጥቂት ፀብ በቀር ሰላም ነበር።

፳፫ እናም በሰባ ዘጠነኛው ዓመት ኃያል የሆነ ጥል ተጀመረ። ነገር ግን እንዲህ ሆነ ኔፊና፣ ሌሂ፣ እናም ብዙዎቹ ወንድሞቻ ቸው ስለእምነቱ እውነት የሆነውን ነጥብ የሚያውቁት፣ በየቀኑ ብዙ ᐟራዕዮችን ይመ ለከቱ የነበሩ፤ ስለሆነም ለህዝቡ ሰበኩ፣

፲፫ ᐟ ፩ ነገሥ. ፲፰፡፩፣ ፳–፳፮።
፲፬ ᐟ ሔለ. ፲፩፡፬።
፲፯ ᐟ ዘዳግ. ፲፩፡፲፫–፲፯።
፲፰ ᐟ ሔለ. ፲፡፲–፲፩።
፲፱ ᐟ ሔለ. ፲፡፲–፲፩።
፳ ᐟ ሔለ. ፲፡፩–፳፬።
፳፩ ᐟ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን።
፳፫ ᐟ አልማ ፳፭፡፳፪፣ ት. እና ቃ. ፪፯፡፲፱።

በዚሁ ዓመት ሰዎቹ ጥሉን እንዲያቆሙ አደረጉ።

፳፬ እናም እንዲህ ሆነ በኔፊ ህዝብ ላይ በመሣፍንቱ የሰማንያ ዓመት የንግስ ዘመን ከጥቂት ዓመታት በፊት ወደላማናውያን የሄዱ፣ ያልታወቀ ቁጥር የነበራቸው ተቃዋሚ የኔፊ ሰዎች ነበሩ፤ እናም የላማናውያንን ስም ለራሳቸው ወስደው ነበር፤ እናም ደግሞ ቁጥራቸው ያልታወቀው እውነተኛ የላማናውያን ዝርያዎች፣ በእነርሱ በቁጣ እንዲነሳሱ ተደረጉ፣ ስለዚህ ከወንድሞቻቸው ጋር ጦርነት ጀመሩ።

፳፭ እናም ግድያን እንዲሁም ዝርፊያን ፈፀሙ፤ እናም ወደ ተራራውና፣ ምድረበዳው እንዲሁም ሚስጥራዊ ስፍራዎች እያፈገፈጉ፣ ሊገኙ እንዳይችሉም እራሳቸውን ደበቁ፤ ተቃዋሚዎች ወደ እነርሱ ስለሚመጡ ተጨማሪዎችንም በየቀኑ ተቀበሉ።

፳፮ እናም ከጊዜ በኋላ፣ አዎን፣ በትንሽ ዓመታትም፣ እጅግ ታላቅ የሌቦች ቡድን ሆኑ፤ እናም የጋድያንቶንን ሚስጥራዊ አሴር በሙሉ ፈልገው አገኙ፤ እንደዚህም የጋድያንቶን ዘራፊዎች ሆኑ።

፳፯ አሁን እነሆ፣ እነዚህ ሌቦች ታላቅ ጥፋትን፤ አዎን፣ በኔፊ ሰዎች መካከልም፣ እናም ደግሞ በላማናውያን ሰዎች መካከል እንኳን ታላቅ ጥፋትን ሰሩ።

፳፰ እናም እንዲህ ሆነ ለዚህ የጥፋት ሥራ ማቆሚያ ማድረግ አስፈላጊ ነበር፤ ስለዚህ እነርሱ ወደ ምድረበዳው፣ እናም በተራራው እነዚህን የሌቦች ቡድን እንዲያገኙ እንዲሁም እንዲያጠፉ ጠንካራ ወታደሮችን ላኩ።

፳፱ ነገር ግን እነሆ፣ እንዲህ ሆነ በዚሁ ዓመት ወደራሳቸው ምድርም በመነዳት ተመልሰው ነበር። እናም በኔፊ ህዝብ ላይ የመሣፍንቱ ሰማንያኛው ዓመት የንግስና ዘመን በዚሁ ተፈፀመ።

፴ እናም እንዲህ ሆነ በሰማንያ አንደኛው ዓመት መጀመሪያ ወታደሮቹ በእነዚህ የዘራፊዎች ቡድን ላይ ሄዱ፤ ብዙዎችንም አጠፉ፤ እናም ደግሞ እነርሱም እጅግ ብዙ በሆነ ጥፋትም ተጎብኝተው ነበር።

፴፩ እናም ተራራውን እንዲሁም ምድረበዳውን የወረሩት የዘራፊዎች ቁጥር እጅግ ብዙ ስለነበር ወታደሮቹ ከምድረበዳው እንዲሁም ከተራራው ወጥተው ወደራሳቸው ምድር እንዲመለሱ ተገድደው ነበር።

፴፪ እናም እንዲህ ሆነ ይህ ዓመትም በዚሁ ተፈፀመ። እናም ዘራፊዎቹ አሁንም በጣም ጨመሩና፣ እየበረቱ ሄዱ፣ ስለዚህ የኔፊንና፣ ደግሞ የላማናውያንን ወታደሮች በሙሉ ተቋቋሟቸው፤ እናም በምድሪቱ ሰዎች ላይ ሁሉ ታላቅ ፍርሃት እንዲመጣ አደረጉ።

፴፫ አዎን፣ የምድሪቱን ብዙ ክፍሎች ጎበኝተዋል፣ እናም በእነርሱ ላይም ታላቅ ጥፋትን አድርገዋልና፤ አዎን ብዙዎችንም ገድለው ነበር፣ እናም ሌሎችንም፣ አዎን፣ በተለይም ሴቶቻቸውን እንዲሁም ህፃናት ልጆቻቸውን በምርኮ ወደ ምድረበዳው ወስደዋቸዋል።

፴፬ እንግዲህ በክፋታቸው የተነሳ በህዝቡ ላይ የመጣው ይህ ታላቅ ጥፋት እርሱም ጌታ አምላካቸውን እንዲያስታውሱ አደረጋቸው።

፴፭ እናም የመሣፍንቱ ሰማንያ አንደኛ ዓመት የንግስና ዘመን በዚሁ ተፈፀመ።

፴፮ እናም በሰማንያ ሁለተኛው ዓመት በድጋሚ ጌታ አምላካቸውን ᐧመርሳት ጀመሩ። እናም በሰማንያ ሶስተኛው ዓመት በክፋታቸው መጠናከር ጀመሩ። እናም በሰማንያ አራተኛው ዓመት መንገዳቸውን አላሻሻሉም ነበር።

፴፯ እናም እንዲህ ሆነ በሰማንያ አምስተኛው ዓመት በኩራታቸውና፣ በክፋታቸው እየበረቱ ሄዱ፤ እናም እንደገና ለመጥፋትም እንደዚህ ደርሰው ነበር።

፴፰ እናም ሰማንያ አምስተኛው ዓመትም በዚሁ ተፈፀመ።

ምዕራፍ ፲፪

ሰዎች ያልተረጋጉ እናም፣ ሞኞች፣ እንዲሁም ክፋትን ለመስራት የፈጠኑ ናቸው—ጌታ ህዝቡን ይገስጻል—የሰዎች ከንቱነት ከእግዚአብሔር ኃይል ጋር ተነፃፀረ—በፍርድ ቀን ሰዎች የዘለዓለም ህይወትን ወይንም የዘለዓለም ፍርድን ያገኛሉ። በ፯ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም የሰው ልጆች እንዴት ሀሰተኞች፣ እናም ደግሞ ልባቸው ያልተረጋጋ መሆኑን ለመመልከት እንችላለን፤ አዎን፣ ጌታም [ሀ]እምነታቸውን በእርሱ ላደረጉ መጨረሻ በሌለው ቸርነቱ ሲባርካቸውና፣ [ለ]ሲያበለፅጋቸው ለመመልከት እንችላለን።

፪ አዎን፣ እናም በመስካቸውም ላይ ከብቶቻቸውንና፣ መንጋዎቻቸውን፣ በወርቃቸውም፣ በብራቸውም፣ እናም ሁሉንም ዓይነት የከበሩ ነገሮቻቸውን በሚያበዛላቸው ህዝቡን እናያለን፤ ህይወታቸውን በማትረፍና፣ ከጠላቶቻቸው እጅ እነርሱን በማስለቀቅም፤ ጠላቶቻቸው በእነርሱ ላይ ጦርነት እንዳያውጁ ልባቸውን በሚያራራበት፤ አዎን፣ እናም በአጠቃላይ ለህዝቡ ደህንነትና ደስታ ሁሉንም ነገሮች በሚያደርግበት ጊዜ፤ አዎን ይህም [ሀ]ልባቸውን የሚያጠጥሩበትና፣ ጌታ አምላካቸውን የሚረሱበት፣ ቅዱስ የሆነውንም በእግራቸው [ለ]የሚረግጡበት ጊዜ ነው—አዎን፣ ይህም የሆነበት ምክንያት ሰዎቹ ስለተመቻቹ፣ እናም እጅግ በታላቅ ሁኔታ ስለበለፀጉ ነው።

፫ እናም ጌታ ህዝቡን በብዙ ስቃይ [ሀ]ካል ገሰጻቸው፤ አዎን፣ በሞትና በፍርሃትና፣ በረሃብ እናም በሁሉም ዓይነት ቸነፈር ካልጎበኛቸው በስተቀር እርሱን [ለ]እንደማያስታውሱት እናያለን።

፬ አቤቱ የሰው ልጆች እንዴት ሞኞችና፣ ከንቱዎችና፣ ክፉዎች፣ እንዲሁም ዲያብሎስን ተከታዮች፣ እናም እንዴት ኃጢያትን ለመስራት [ሀ]ፈጣንና፣ መልካምን ለማድረግ እንዴት የዘገዩ ናቸው፤ አዎን የዚያን ክፉ የሆነውን ቃላት ለመስማት፣ እናም በዓለም ከንቱ ነገሮች ላይ [ለ]ልባቸውን ለማድረግ እንዴት ፈጣን ናቸው!

፭ አዎን፣ [ሀ]በኩራት ለመወጠር ምንኛ ፈጣን ናቸው፤ አዎን፣ ለጉራና፣ ክፉ የሆኑትን ነገሮች ሁሉ ለማድረግ ምንኛ ይፈጥናሉ፤ እናም ጌታ አምላካቸውን ለማስታወስና፣ ለምክሮቹ ጆሮአቸውን ለመስጠት እንዴት ይዘገያሉ፣ አዎን በጥበብ ጎዳናስ [ለ]ለመራመድ እንዴት ያዘግማሉ!

፮ እነሆ፣ እነርሱን [ሀ]የፈጠረው ጌታ አምላካቸው፣ በእነርሱ ላይ [ለ]እንዲገዛና እንዲነግስ አይፈልጉም፤ ታላቅ ቸርነትና ምህረት በእነርሱ ላይ ቢኖረውም ምክሩን ችላ ይሉታል፤ እናም መሪያቸው እንዲሆን አልፈለጉም።

፯ አቤቱ የሰው ልጆች [ሀ]ከንቱነት እንዴት ታላቅ ነው፣ አዎን ከመሬት ትቢያ እንኳን ያነሱ ናቸው።

፰ እነሆም፣ በታላቁ እና በዘለዓለማዊው አምላካችን ትዕዛዝ የምድር ትቢያ እስከሚ ከፈል ወዲህና ወዲያ ይንቀሳቀሳል።

፱ አዎን፣ እነሆ በድምጹ ኮረብቶችና፣ እና ተራሮች ይናወጣሉ፣ እናም [ሀ]ይንቀጠቀጣሉ።

፲ እናም በድምፁም [ሀ]ኃይል ይሰባበራሉና፣ የተስተካከሉ ይሆናሉ፤ አዎን፣ እንደ ሸለቆም ይሆናሉ።

፲፪ ፩ *ሀ* መዝ. ፴፯፡ ፯–፰፤ ፪ ኔፊ ፳፪፡ ፪፤ ሞዛያ ፪፡ ፯። ቅ.መ.መ. መታመን። *ለ* ፪ ዜና ፳፯፡ ፩፤ መዝ. ፩፡ ፪–፫። ፪ *ሀ* ቅ.መ.መ. ክህደት። *ለ* አልማ ፭፡ ፶፫፤ ፫ ኔፊ ፳፰፡ ፴፭። ፫ *ሀ* ሞዛያ ፳፫፡ ፳፩፤ ት. እና ቃ. ፶፰፡ ፳፩፤ ፻፩፡ ፰። *ለ* ዓሞ. ፪፡ ፯–፲፩። ፬ *ሀ* ዘፀአ. ፴፪፡ ፰። *ለ* ማቴ. ፲፭፡ ፲፱፤ ዕብ. ፫፡ ፲፪። ፭ *ሀ* ምሳ. ፳፱፡ ፳፫። ቅ.መ.መ. ኩራት። *ለ* ቅ.መ.መ. መራመድ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መራመድ (መሄድ)። ፮ *ሀ* ኢሳ. ፴፭፡ ፱፤ ት. እና ቃ. ፶፰፡ ፴፤ ሙሴ ፯፡ ፴፪–፴፫። *ለ* ት. እና ቃ. ፳፡ ፱። ፯ *ሀ* ኢሳ. ፴፡ ፲፭፣ ፲፯፤ ሞዛያ ፪፡ ፲፱፤ ሙሴ ፩፡ ፲። ፱ *ሀ* ፫ ኔፊ ፳፪፡ ፲። ፲ *ሀ* ፩ ኔፊ ፲፯፡ ፴፯።

፲፩ አዎን፣ በድምፁም ኃይል ᵐመላዋ ምድር ትንቀጠቀጣለች፤

፲፪ አዎን፣ በድምፁም ኃይል፣ የመሠረት ድንጋዮችም ከመሃላቸው ይናወጣሉ።

፲፫ አዎን፣ እናም ምድርንም ተንቀሳቀሽ ቢላት—ትንቀሳቀሳለች።

፲፬ አዎን፣ ᵐምድሪቱን—ቀኑ ለብዙ ሰዓታት ᵃይረዝም ዘንድ ወደኋላ ᵐተመለሽ ቢላት—ይህም ይሆናል፤

፲፭ እናም እንደ ቃሉ መሰረት ምድር ወደ ኋላ ትጓዛለች፤ ለሰውም ፀሐይ የቆመች ሆና ትታያለች፤ አዎን፣ እናም እነሆ፣ ይህም እንዲህ ነው፤ በእርግጥም መሬት ትንቀሳቀሳለች እንጂ ፀሐይ አይደለችምና።

፲፮ እናም እነሆ፣ ደግሞ ታላቁ ጥልቅ የሆነውን ᵐውሀም—ᵃድረቅ ቢለው—ይደርቃል።

፲፯ እነሆ፣ ይህንን ተራራ—ᵐተነስ እናም በከተማዋ ላይ እንድትቀበር ውደቅ ቢለው—እነሆ ይሆናል።

፲፰ እናም እነሆ፣ አንድ ሰው በምድር ውስጥ ሀብቱን ቢቀብርና ጌታ ᵐበደበቀው ክፋት የተነሳ ᵃየተረገመ ይሁን ቢለው፣ እነሆ፣ የተረገመ ይሆናል።

፲፱ እናም ጌታ—ማንም ሰው ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እስከዘላለሙ እንዳያገኘህ የተረገምህ ሁን ቢለው—እነሆ፣ ማንም ሰው ከዚህ ጊዜ ጀምሮ፣ እናም እስከዘላለሙ አያገኘውም።

፳ እናም እነሆ፣ ጌታ አንድን ሰው—በክፋትህ የተነሳ ለዘለዓለም የተረገምህ ትሆና ለህ ቢለው—ይህም ይሆናል።

፳፩ እናም ጌታ—በክፋታችሁ የተነሳ ከፊቴ ትለያላችሁ ቢል—እንዲያ እንዲሆን ያደርጋል።

፳፪ እናም ይህን ለሚለው ለእርሱ ወዮ ለት፤ ምክንያቱም ክፋትን ለሚያደርግ ይሆናል፤ እናም ሊድን አይቻለውም፤ ስለዚህ፣ በዚህም የተነሳ፣ ሰዎች እንዲድኑ ዘንድ፣ ንስሃም ታውጇል።

፳፫ ስለዚህ፣ ንስሃ የገቡ፣ እናም የጌታ የአምላካቸውን ድምፅ የሰሙ የተባረኩ ናቸው፤ ᵐየሚድኑትም እነዚህ ናቸውና።

፳፬ እናም እግዚአብሔር በታላቁ ሙላቱ ሰዎች ወደ ንሰሃ እና መልካም ሥራዎች ይመጡ ዘንድ፣ እንደሥራቸውም ከፀጋም ወደ ᵐፀጋ ይመልሳቸው ዘንድ ያድርግላቸው።

፳፭ እናም ሰዎች ሁሉ እንዲድኑ እፈልጋለሁ። ነገር ግን በታላቁ እና በመጨረሻው ቀን የሚጣሉ አዎን፣ ከጌታ ፊት የሚጣሉ፣ ጥቂቶች እንዳሉ አንብበናል፤

፳፮ አዎን፣ እነርሱም መልካም የሚያደርጉ ᵐዘለዓለማዊ ህይወት ይኖራቸዋል፤ እናም ክፉ የሚያደርጉ ለዘለዓለም ይፈረድባቸኋል የሚለውን ቃል ለማሟላት ወደ ዘለዓለማዊው ᵃስቃይ ይላካሉ። እናም ይህ ነው። አሜን።

የላማናዊው ሳሙኤል ለኔፋውያን የሰጠው ትንቢት።

ምዕራፍ ፲፫ እስከ ፲፭ አጠቃሎ የያዘ።

ምዕራፍ ፲፫

ላማናዊው ሳሙኤል ኔፋውያን ንስሃ ካልገቡ በቀር እንደሚጠፉ ተነበየ—እነርሱ እና ሀብታቸው የተረገሙ ናቸው—ነቢያትን አልተቀበሉአቸውም እናም በድንጋይ ወገሩአቸው፤ እነርሱም በአጋንንት ተከበቡ፣ እናም ክፋትን በመፈፀም ደስ ታን ፈለጉ። በ፲፯ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንግዲህ እንዲህ ሆነ በሰማንያ

፲፩ ᵐ ሞር. ፭፡፳፫፣ ኤተር ፱፡፱።
፲፱ ᵐ ኢያ. ፲፡፲፪–፲፱። ᵃ ፪ ነገሥ. ፳፡፰–፲፩። ᵇ ሐ ኢሳ. ፴፰፡፭–፰።
፲፯ ᵐ ማቴ. ፰፡፳፯።
ᵃ ኢሳ. ፵፡፳፣ ፶፩፡፲። ᵇ ፲፯ ᵐ ᵉ ኔፊ ፰፡፲።
፲፰ ᵐ ሞር. ፩፡፲፰፣ ኤተር ፲፡፩። ᵃ ሔለ. ፲፫፡፲፯።
፳፣ ᵐ ቅ.መ.መ. ደህንነት።
፳፡ ᵐ ቅ.መ.መ. ፳፣ ፳፡ ᵐ ማቴ. ፳፭፡፴፣ ዮሐ. ፭፡፳፰–፳፱፣ ሮሜ ፮፡፲ᵐ። ᵃ ቅ.መ.መ. ኩነኔ።

ስድስተኛው ዓመት ᵐላማናውያን በሙሴ ህግ መሰረት የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ለመጠበቅ ጠንቃቆች በሆኑበት ጊዜ፣ ኔፋ ውያን በክፋታቸው፣ አዎን በታላቅ ክፋት ነበሩ።

፪ እናም እንዲህ ሆነ በዚህ ዓመት፣ ሳሙ ኤል የሚባል አንድ ላማናዊ ሰው ነበር፣ እር ሱም ወደ ዛራሔምላ ምድር መጣና ለህዝቡ መስበክ ጀመረ። እናም እንዲህ ሆነ ለብዙ ቀናትም ህዝቡን ስለንስሃ ሰበከ፣ እናም እነርሱ ግን አስወገዱትና፣ እርሱ ወደራሱ ምድር ለመመለስ ተቃርቦ ነበር።

፫ ነገር ግን እነሆ፣ እንደገና እንዲመለስ ዘንድ፣ እናም ወደ ᵐልቡ የመጡትን ነገ ሮች ለህዝቡ መተንበይ እንዳለበት የጌታ ድምፅ ወደእርሱ መጣ።

፬ እናም እንዲህ ሆነ እነርሱም ወደ ከተ ማው እንዲገባ አልፈቀዱለትም ነበር፤ ስለ ዚህ ሄደ እናም በግንብ ላይ ቆመና፣ እጁን ዘረጋ፣ እናም በኃይል ጮኸና፣ ጌታ በልቡ ያመጣለትን ማናቸውንም ነገሮች ተነበየ።

፭ እናም እንዲህ አላቸው፥ እነሆ፤ እኔ ላማናዊው ሳሙኤል፣ ጌታ በልቤ ያስ ቀመጣቸውን ቃላት እናገራለሁ፤ እናም እነሆ ለዚህም ህዝብ የፍትህ ጎራዴ በዚህ ህዝብ ላይ ትሆናለች እንድልም በልቤ አስ ቀመጠ፤ እናም ᵐየፍትህ ጎራዴ በዚህ ህዝብ ላይ ካልሆነች በስተቀር አራት መቶ ዓመ ታት አያልፉም።

፮ አዎን፣ ይህን ህዝብ ኃያል የሆነው ᵐጥፋት ይጠብቀዋል፤ በእርግጥም በዚህ ህዝብ ላይ ይመጣል፣ እናም ንስሃና፣ በእ ርግጥ ወደዚህ ዓለም በሚመጣውና፣ በብዙ ነገሮች ለሚሰቃየው፣ እንዲሁም ለህዝቡም በሚሞተው በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እም ነት ካልሆነ በቀር ይህን ህዝብ ምንም ሊያ ድን አይችልም።

፯ እናም እነሆ፣ ᵐየጌታ መልአክ ለእኔ ይህን ነገረኝና፣ ለነፍሴም መልካም የምስ ራች አመጣልኝ። እናም እነሆ ᶮመልካሙ የምስራች ይኖራችሁ ዘንድ ለእናንተ እን ድገልፅ ተልኬ ነበር፤ ነገር ግን እነሆ እኔን አልተቀበላችሁኝም።

፰ ስለዚህ፣ ጌታም እንዲህ ይላል፥ የኔፊ ሰዎች ልብ በመጠጠሩ፣ ንስሃ ካልገቡ ቃሌን ከእነርሱ እወስዳለሁ፣ መንፈሴንም ከእነርሱ ᵐአርቃለሁ፣ እናም ከዚህ ወዲያ አልታገስም፣ የወንድሞቻቸውን ልብ በእ ነርሱ ላይ አዞራለሁም።

፱ እናም እንዲመቱ ከማድረጌም በፊት ᵐአራት መቶኛው ዓመት አያልፍም፤ አዎን፣ በጦርነትና በረሃብ፣ እናም በቸነ ፈር እጎበኛቸዋለሁ።

፲ አዎን፣ በኃያሉ ቁጣዬም እጎበኛቸዋ ለሁ፣ እናም የእናንተን ፍፁም ጥፋት የሚ መለከቱ ᵐአራተኛ ትውልድ የሆኑት ጠላ ቶቻችሁ በህይወት ይኖራሉ፤ እናም ንስሃ ካልገባችሁ በእርግጥ ይህ ይሆናል ይላል ጌታ፤ እናም የአራተኛውም ትውልድ ጥፋ ታችሁን ይጎበኛሉ።

፲፩ ነገር ግን ንስሃ የምትገቡ እናም ወደ ጌታ አምላካችሁ ᵐየምትመለሱ ከሆነ፣ እኔም ቁጣዬን ከእናንተ አርቃለሁ ይላል ጌታ፤ አዎን ጌታም እንዲህ ይላል፣ ንስሃ የሚገቡና ወደ እኔ የሚመለሱ የተባረኩ ናቸው፣ ነገር ግን ንስሃ ለማይገቡት ወዮ ላቸው።

፲፪ አዎን፣ ለዚህች ለታላቋ የዛራሔምላ ከተማ ᵐወዮላት፤ እነሆም ፃድቃን በሆኑት ምክንያት ነው የዳነችው፤ አዎን፣ ለዚህች ታላቅ ከተማ ወዮላት ይላል ጌታ፤ ብዙ ዎች፣ አዎን፣ የዚህች የታላቋ ከተማ አብ ዛኛው ክፍል የሚሆኑት በእኔ ላይ ልባቸ ውን እንደሚያጠጥሩ አስተውላለሁ፣ ይላል ጌታ።

፲፫ ነገር ግን ንስሃ የሚገቡት የተባረኩ

፲፫ ፩ ሀ ሔለ. ፲፭፡፱–፳፡
፫ ሀ ት.እና ቃ. ፻፡፭፡
፭ ሀ አልማ ፳፡፳፱፣
፫ ኔፊ ፪፡፲፱፡
፯ ሀ አልማ ፶፭፡፲–፲፱፣
ሔለ. ፲፭፡፲፯፡
፯ ሀ አልማ ፲፫፡፳፯፡
ለ ኢሳ. ፶፪፡፯፡
፳ ሀ ሔለ. ፯፡ ፴፭፡
፱ ሀ አልማ ፶፭፡፲–፲፪፡
፲ ሀ ፩ ኔፊ ፲፪፡፲፪፣
፪ ኔፊ ፳፯፡፱፣
፫ ኔፊ ፳፯፡ ፴፪፡
፲፩ ሀ ፫ ኔፊ ፲፡፭–፯፡
፲፪ ሀ ፫ ኔፊ ፳፡ ፳፡ ፳፱፡ ፱፡፫፡

ናቸው፤ ምክንያቱም እነርሱን አድናቸ ዋለሁና። ነገር ግን እነሆ፣ በዚህች ታላቅ ከተማ ስላሉት ስለ ፃድቃኖች ባይሆን ኖሮ፤ እነሆ፣ [ሀ]እሳት ከሰማይ እንዲወርድ እናም እንዲያጠፋቸው ባደረግሁ ነበር።

፲፬ ነገር ግን እነሆ፣ ስለ ፃድቃን ሲባል ነው የዳነው። ነገር ግን እነሆ ፃድቃኖችን ከመካ ከላችሁ የምትወረውሩበት ጊዜ ይመጣል፣ ከዚያም ለጥፋት የበሰላችሁ ትሆናላችሁ ይላል ጌታ፤ አዎን በውስጧ ባሉት ክፋ ትና ርኩሰት የተነሳ ለዚህች ከተማ ወዮላት።

፲፭ አዎን፤ እናም የጌዴዎን ከተማ በው ስጧ ስላለው ክፋትና እርኩሰት ወዮላት።

፲፮ አዎን፣ እናም በኔፋውያን በተያዙት ከተሞችና በዙሪያቸው ላሉት ሁሉ በክፋ ታቸው እንዲሁም በርኩሰታቸው የተነሳ ወዮላቸው።

፲፯ እናም እነሆ፣ በምድሪቱ ላይ ባሉት በሰዎቹ ድርጊትም፣ አዎን፣ በክፋታቸውና በእርኩስነታቸው የተነሳ [ሁ]እርግማን በምድ ሪቱ ላይ ይመጣል ይላል የሰራዊት ጌታ።

፲፰ እናም እንዲህ ይሆናል ይላል የሰራ ዊት ጌታ፤ አዎን፣ ታላቁና እውነተኛው አምላካችን፣ በምድሪቱም ታላቅ እርግ ማን በመሆኑ በምድር ውስጥ ሀብት [ሂ]የቀ በረ ፃድቅ ካልሆነና የደበቀው ለጌታ ካል ሆነ መልሶ አያገኘውም።

፲፱ ሀብታቸውን ወደ እኔ እንዲደብቁት እፈልጋለሁና፣ አለ ጌታ፤ እናም ሀብታ ቸውን ለእኔ ለማይደብቁት እርግማን ይሆ ንባቸዋል፤ ፃድቃኖች ካልሆኑ በቀር ንብ ረታቸውን ወደ እኔ አይደብቁምና፤ እናም ወደ እኔ ንብረቱንም የማይደብቅ፣ እርሱና፣ ደግሞ ንብረቱ፣ የተረገመ ነው፤ እናም ምድሪቱ በመረገሟ ማንንም አያድነውም።

፳ እናም ልባቸውን በሀብታቸው ላይ በማድረጋቸው ንብረታቸውን የሚደብቁ በት ቀን ይመጣል፤ እናም ልባቸውን በሀብ ታቸው ላይ በማድረጋቸውና ከጠላቶቻቸው ሲሸሹ ንብረታቸውን ስለሚደብቁ፤ ወደ እኔም ስለማይደብቋቸው፣ እነርሱም ሆኑ ንብረቶቻቸው የተረገሙ ይሁኑ፤ በዚያም ቀን ይመታሉ ይላል ጌታ።

፳፩ እነሆ እናንተ፣ የዚህች ታላቅ ከተማ የሆናችሁ ሰዎች፣ እናም ቃሌን አድምጡ፤ አዎን፣ ጌታ የተናገራቸውንም ቃላት [ሁ]አድ ምጡ፤ እነሆም እንዲህም አለ፥ በሀብታች ሁም የተረገማችሁ ናችሁ፤ እናም ደግሞ በእነርሱ ላይ ልባችሁን ስላደረጋችሁና ለእ ናንተ እነዚህን የሰጣችሁንም የእርሱን ቃላት ስላላዳመጣችሁ ሀብታችሁ ተረግመዋል።

፳፪ ጌታ አምላካችሁን በተባረካችሁ በትም ሁኔታ አታስታውሱትም፤ ነገር ግን ጌታ አምላካችሁን ባታመሰግኑበትም ሁልጊዜ [ሀ]ሀብታችሁን ታስታውሳላችሁ፤ አዎን ልባችሁ ወደጌታ አልተወሰደም፣ ነገር ግን [ለ]ለጉራና ለመወጣጠር፣ [ሐ]ለቅና ቶች፣ ለፀብ፣ ለተንኮል፣ ለስደትና፣ ለግ ድያ፣ እናም ለሁሉም ዓይነት ክፋት በኩ ራት ያብጣል።

፳፫ በዚህም የተነሳ ጌታ እግዚአብሔር በምድሪቱ ላይ፣ እናም ደግሞ በሀብታችሁ ላይ እርግማን እንዲመጣ ያደርጋል፣ እናም ይህ የሆነው በክፋታችሁ ነው።

፳፬ አዎን፣ በደረሰው በዚህ ጊዜ፣ ነቢ ያቱን [ሀ]በማባረራቸውና፣ በመሳለቃቸው፣ እናም በድንጋይ በመውገራቸውና፣ በመ ግደላቸው፣ እንዲሁም እንደጥንት ጊዜ ውም እንዳደረጉት ሁሉንም ዓይነት ክፋት በማድረጋቸው ለዚህ ህዝብ ወዮለት።

፳፭ እናም እንግዲህ በምትናገሩ ጊዜም እንዲህ ብላችኋል፥ ጊዜአችን እንደ ጥንቱ እንደ [ሀ]አባቶቻችን ጊዜ እንኳን ቢሆን ነቢ ያቶቹን አንገድላቸውም ነበር፤ በድንጋይም አንወግራቸውም ነበር፣ እናም አንወረው ራቸውም ነበር።

፲፫ ሀ ዘፍጥ. ፲፱፡፳፬፤ ፳፪፤ ፪ ነገሥ. ፩፡፱–፲፯፣ ፲ ኔፊ ፱፡፲፩።
፲፯ ሀ ሔለ. ፲፪፡፲፰።
፲፰ ሀ ሞር. ፩፡፲፰፣ ኤተር ፲፡፩።
፲፱ ሀ ቅ.መ.መ. ማዳመጥ።
፳፪ ሀ ሉቃ. ፲፪፡፴፬። ቅ.መ.መ. ሀብቶች፤ አለማዊነት።
ለ ቅ.መ.መ. ኩራት።
ሐ ቅ.መ.መ. ቅናት።
፳፫ ሀ ፪ ዜና ፴፮፡፲፭–፲፯፣ ፩ ኔፊ ፩፡፳።
፳፭ ሀ የሐዋ. ፯፡፶፩።

፳፮ እነሆ እናንተ ከእነርሱ የከፋችሁ ናችሁ፤ ምክንያቱም ጌታ ህያው እንደ ሆነ ስለኃጢአታችሁ እንዲሁም ስለክፋ ታችሁ ለመመስከር የጌታን ቃል ለእናንተ ለመናገር በመካከላችሁ ᵐነቢይ ከመጣ፣ በእርሱ ᵃትቆጣላችሁም፣ ታባርሩታላች ሁም፣ እናም እርሱን ለማጥፋት ሁሉንም ዓይነት መንገድ ትሻላችሁ፤ አዎን፣ ስራ ችሁ መጥፎ መሆኑን ᵇበመመስከሩ እርሱ ሀሰተኛ ᶜነቢይና፣ ኃጢአተኛ፣ እንዲሁም የዲያብሎስ ነው ትላላችሁ።

፳፯ ነገር ግን እነሆ፣ አንድ ሰው ከመካከ ላችሁ ከመጣና ይህንን አድርጉ፣ ኃጢአት አይደለም፣ አድርጉትና አትሰቃዩም ካላ ችሁ፣ አዎን እንዲህም ይላል፥ በልባችሁ ኩራትም ተመሩ፤ አዎን፣ በዐይኖቻችሁ ኩራትም ተመሩ፤ እናም ልባችሁ እንደፈ ቀደም አድርጉ—እናም አንድ ሰው በመካ ከላችሁ ከመጣና እንዲህ ቢላችሁ፥ እርሱን ትቀበሉታላችሁ፣ ᵐነቢይ ነውም ትሉታላ ችሁ።

፳፰ አዎን፣ እርሱን ታወድሱታላችሁ፣ እናም ለእርሱም ካላችሁ ቁሳቁሶች ትሰ ጡታላችሁ፣ ከወርቃችሁና ከብራችሁም ትሰጡታላችሁ፣ እንዲሁም ውድ የሆኑ ልብሶችም ታለብሱታላችሁ፤ እናም ᵐሸን ጋይ የሆኑ ቃላት ለእናንተ በመናገሩና፣ ሁሉም መልካም ነው በማለቱ፣ በእርሱ ዘንድ ስህተት አታገኙም።

፳፱ አቤቱ እናንተ ኃጢአተኛና ጠማማ ትውልዶች፣ እናንተ ጠማሮችና አንገተ ደንዳና የሆናችሁ ሰዎች፣ ጌታ ምን ያህል ጊዜ ይታገሰናል ብላችሁ ትገምታላችሁን? አዎን፣ ᵐበሞኝ እናም ᵃበእውር መሪስ ለምን ያህል ጊዜ እንድትመሩ ትፈቅዳላችሁን? አዎን፣ ለምን ያህል ጊዜስ ነው ከብርሃን ይልቅ ᵃጨለማን ᵐየምትመርጡት?

፴ አዎን፣ እነሆ የጌታ ቁጣ በእናንተ ላይ ነዷል፤ እነሆ፣ ምድሪቱንም በክፋታችሁ የተነሳ ረግሟታል።

፴፩ እናም እነሆ፣ ሀብታችሁን መያዝ እንዳትችሉ ከእጃችሁ ᵐእንዲያመልጥ የሚረግምበት ጊዜ ይመጣል፤ እናም በድ ህነታችሁም ወቅት መልሳችሁ አታገኙ ትም።

፴፪ እናም በድህነታችሁም ቀን ወደ ጌታ ትጮኻላችሁ፤ የመውደሟያችሁ ጊዜ ስለ ደረሰባችሁና ጥፋታችሁም እርግጥ በመ ሆኑ በከንቱ ትጮኻላችሁም፤ እናም በዚ ያን ቀን ታለቅሳላችሁና ትጮኻላችሁ አለ የሰራዊት ጌታ። ታለቅሳላችሁም፣ እንዲ ህም ትላላችሁ፥

፴፫ አቤቱ ᵐንስሃ ብገባና፣ ነቢያቱንም ባልገድል፣ እናም በድንጋይ ᵃባልወግርና፣ ባልወረውራቸው እመኝ ነበር። አዎን፣ በዚያን ቀን እንዲህ ትላላችሁ፥ አቤቱ ሀብ ታችንን በሰጠን ቀን ጌታ አምላካችንን ብና ስታውስ ኖሮ፣ እናም እንዳናጣቸው ከእጃ ችን አያመልጡም ነበር፤ እነሆ ሀብታችን ከእኛ ሸሽቷልና።

፴፬ እነሆ እዚህ መሳሪያ አስቀምጠናል፣ እናም በሚቀጥለው ቀን የለም፤ እናም እነሆ፣ ለጦርነት ጎራዴዎቻችንንም በፈለ ግናቸው ጊዜ ከእኛ ተወስደዋል።

፴፭ አዎን ንብረቶቻችንን ደብቀናል፣ እናም ምድሪቱም በመረገሟ ጠፍተውብ ናል።

፴፮ የጌታ ቃል ወደ እኛ በመጣ ጊዜ ንስሃ በገባን ኖሮ፤ ምክንያቱም እነሆ፣ ምድሪቱ ተረግማለች፣ እናም ሁሉም ነገር ከእጅ አምላጭ ሆነዋል፣ እኛም ልንይዛቸው አል ቻልንም።

፴፯ እነሆ፣ እኛ በጋኔን ተከበናል፤ አዎን፣ ነፍሳችንን ለማጥፋት በፈለገው መላዕክትም ተከበናል። እነሆ ኃጢአቶቻችን ታላቅ ናቸው። አቤቱ ጌታ፣ ቁጣህን ከእኛ መመ

ᵃ፳፮ ᵐ ፪ ዜና ፲፰፡ ፯፣ ሉቃ. ፲፯፡ ፴፩። ᵃ ኢሳ. ፴፡ ፱–፲። ᵃ ገላ. ፬፡ ፲፯። ᵐ ማቴ. ፲፫፡ ፶፯።

ᵃ፳፯ ᵐ ሚክ. ፪፡ ፲፩። ᵃ ᵐ.ᵐ. የካህን ተንኮል። ᵃ፳፰ ᵐ ፪ ጢሞ. ፬፡ ፫–፬። ᵃ፳፱ ᵐ ፪ ኔፊ ፳፡ ፱። ᵃ ማቴ. ፲፭፡ ፲፬።

ᵃ ሐ ኢዮብ ፳፬፡ ፲፫። ᵐ ዮሐ. ፫፡ ፲፱። ᵃ፴ ᵐ ሞር. ፩፡ ፲፯–፲፡ ። ᵃ፴፫ ᵐ ሞር. ፪፡ ፲–፲፩። ᵃ ማቴ. ፳፫፡ ፴፯።

ለስ አትችልምን? እናም በእነዚያ ቀን የእ
ናንተ ቋንቋ እነዚህ ይሆናሉ።
፴፰ ነገር ግን እነሆ፣ [ሀ]የሙከራ ቀናት
አልፈዋል፤ እስከዘለዓለም ድረስ እስከሚ
ዘገይ እናም መጥፊያችሁ እርግጥ እስከሚ
ሆን ድረስ የመዳኛ ቀናችሁን [ለ]አዘገያችሁ፤
አዎን፣ የህይወት ዘመናችሁን በሙሉ ልታ
ገኙት በማትችሉት ተመኝታችኋል፤ እናም
ታላቅና ዘለዓለማዊው ራስ በሆነው ውስጥ
ባለው የፅድቅ ተፈጥሮ ተቃራኒ በሆነው
ነገር ክፉትን በመስራት [ሐ]ደስታን ተመኝ
ታችኋል።
፴፱ የዚህች ምድር የሆናችሁ ሰዎች፣
አቤቱ ቃሌን እንድታደምጡ እፈልጋ
ለሁ! እናም ንስሃ እንድትገቡና እንድት
ድኑ ዘንድ፣ እናም የጌታ ቁጣ ከእናንተ እን
ዲመለስ ዘንድ እፀልያለሁ።

ምዕራፍ ፲፬

ሳሙኤል በምሽት ብርሃን እንደሚሆን እናም አዲስ ኮከብ በክርስቶስ መወለድ እንደሚሆን ተነበየ—ክርስቶስ ሰዎችን ከጊዜያዊው እንዲሁም ከመንፈሳዊው ሞት ያድናቸዋል—የሞቱም ምልክቶች የሶስት ቀን ጨለማ፣ የአለቶች መፈረካከስ፣ እናም ታላቅ የሆነ የምድር መናወጥን ያጠቃልላል። በ፮ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንግዲህ እንዲህ ሆነ ላማናዊው
[ሀ]ሳሙኤል ሊፃፉ የማይችሉ ከዚህ የበለጡ
ታላቅ ነገሮችን ተንብዮአል።
፪ እናም እነሆ እንዲህም አላቸው፥ እነሆ፣
ምልክትን እሰጣችኋለሁ፤ ከዚህ ወዲያ
አምስት ዓመት ይመጣል፣ እናም እነሆ፣
ከዚያም በስሙ የሚያምኑትን ሁሉ ሊያ
ድናቸው የእግዚአብሔር ልጅ ይመጣል።
፫ እናም እነሆ ይህንን የምሰጣችሁ በመም
ጫው ጊዜ [ሀ]ለምልክት እንዲሆናችሁ ነው፤
እነሆም ከመምጣቱ አንድ ቀን በፊት ባለው
ምሽትም ምንም ዓይነት ጨለማ እስከማይ
ሆን ድረስ በሰማይ ታላቅ ብርሃን ይሆናል፤
ለሰዎችም እንደ ቀን ሆኖ ይታያቸዋል።
፬ ስለዚህ፣ ልክ አንድ ቀን እንደሆነና፣
ምሽት እንደሌለ፣ አንድ ቀንና አንድ ሌሊት
እናም አንድ ቀን ይሆናሉ፤ ይህም ለምል
ክት ይሆናችኋል፤ ምክንያቱም የፀሐይ
መውጫዋንና መጥለቂያዋን ታውቃላች
ሁና፤ ስለዚህ ሁለት ቀንና አንድ ምሽት
እንደሚሆን በእርግጥ ታውቃላችሁ፣ ይሁን
እንጂ ምሽቱ ጨለማ አይሆንም፤ እናም
ይህ [ሀ]እርሱም ከመወለዱ በፊት የሚሆነው
ምሽት ይሆናል።
፭ እናም እነሆ ተመልክታችኋት የማታ
ውቋት አዲስ [ሀ]ኮከብም ትወጣለች፤ እናም
ይህ ለምልክት ይሆናችኋል።
፮ እናም እነሆ፣ ይህ ብቻም አይደለም፤
በሰማይ ብዙ ምልክቶች እንዲሁም አስደ
ናቂ ነገሮች ይሆናሉ።
፯ እናም እንዲህ ይሆናል፥ ሁላችሁም
በመሬት ላይ [ሀ]እስከምትወድቁ ትደነቃላ
ችሁ፣ እንዲሁም ትገረማላችሁ።
፰ እናም እንዲህ ይሆናል፥ በእግዚአብ
ሔር ልጅ [ሀ]የሚያምን ዘለዓለማዊ ህይወት
ይኖረዋል።
፱ እናም እነሆ፣ ስለነዚህም ነገሮች መጥቼ
ለእናንተ እንድናገር ጌታ በመላዕክቱ አዞ
ኛል፤ አዎን እነዚህን ነገሮች ለእናንተ እን
ድተነብይ አዞኛል፤ አዎን፣ እንዲህም ብሎ
ኛል፥ ንስሃ ግቡ እናም የጌታንም መንገድ
አቅኑ ብለህ ለዚህ ህዝብ ጩህ።
፲ እናም እንግዲህ፣ ላማናዊ በመሆኔና
ጌታ ያዘዘኝን ቃላት ለእናንተ በመናገሬ፣
እናም ለእናንተ ቃሉም አስቸጋሪ በመሆኑ፣
በእኔ ተቆጣችሁ፣ እናም እኔን ለማጥፋት
ፈለጋችሁ፤ ከመካከላችሁም [ሀ]አውጥታችሁ
ጥላችሁኛል።

፴፰ ሀ ሞር. ፪፥ ፲፭።
ለ አልማ ፴፬፥ ፴፫–፴፬።
ሐ አልማ ፵፩፥ ፲–፲፩።
፲፬ ፩ ሀ ሔለ. ፲፫፥ ፪።
፫ ሀ ፫ ኔፊ ፩፥ ፲፭።
፬ ሀ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—ስለኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ እና ሞት ትንቢቶች።
፭ ሀ ማቴ. ፪፥ ፩–፪፤
፫ ኔፊ ፩፥ ፳፩።
፯ ሀ ፫ ኔፊ ፩፥ ፲፮–፲፯።
፰ ሀ ዮሐ. ፫፥ ፲፮።
፲ ሀ ሔለ. ፲፫፥ ፪።

፲፬ እናም ቃላቴን ትሰማላችሁ፤ ምክን ያቱም ለዚህ ስል ነው ወደ ከተማዋ ግንብ የመጣሁት፣ ስለዚህ በክፋታችሁም የተነሳ የሚጠብቃችሁን የእግዚአብሔርን ቅጣት ትሰሙት እንዲሁም ታውቁት ዘንድ፤ እናም ደግሞ የንስሃን ሁኔታ እንድታውቁት ዘንድ የመጣሁት፤

፲፭ እናም ደግሞ የእግዚአብሔርን ልጅ፣ የሰማይና የምድር [a]አባት የሆነውን፣ ከመጀመሪያው ጀምሮ የሁሉም ነገሮች ፈጣሪ የሆነውን፣ የኢየሱስ ክርስቶስን መምጣት ታውቁ ዘንድ፤ እናም በስሙም እንድ ታምኑ ባለኝ አላማ፣ የመምጣቱን ምልክ ቶች እንድታውቋቸው መጣሁ።

፲፮ እናም በስሙ [b]ካመናችሁ፣ [c]በመልካ ምነቱ ለእነዚህ ስርየትን ታገኙ ዘንድ ለኃ ጢአታችሁ ሁሉ ንስሃን ትገባላችሁ።

፲፯ እናም እነሆ፣ በድጋሚ ሌላ ምልክት እሰጣችኋለሁ፤ አዎን፣ የሞቱን ምልክት።

፲፰ እነሆም፣ [d]ደህንነት እንዲመጣ በእር ግጥ መሞት ይገባዋል፤ አዎን፣ ሞቱ ሰዎች በጌታ ፊት እንዲቀርቡ የሙታን [e]ትንሳ ኤን እንዲያመጣ ጠቃሚ እንዲሁም አስ ፈላጊ ይሆናል።

፲፱ አዎን፣ እነሆ፣ ይህ ሞት ትንሳ ኤን ያመጣል፣ እናም የሰው ዘር የሆኑትን በሙሉ ከፊተኛው ሞት [f]ያድናል—መንፈ ሳዊ ከሆነው ሞት፣ የሰው ዘር በሙሉ [g]በአ ዳም መውደቅ ከጌታ ፊት [h]ተለይተዋል፣ በጊዜያዊም በመንፈሳዊም [i]ሞት እንደ ሞቱ ናቸው።

፲፳ ነገር ግን እነሆ፣ የክርስቶስ ትንሣኤ የሰው ዘርን፣ አዎን፣ የሰው ዘርን በሙሉ [j]ያድናል፣ እናም ወደ ጌታ ፊትም ያቀር ባቸዋል።

፲፳፡ አዎን፣ እናም የንስሃንም አካሄድ ያመጣል፤ ንስሃ የሚገባ ቢኖር አይቆረጥ ምና ወደ እሳቱም አይወረወርም፤ ነገር ግን ንስሃ የማይገባ ይቆረጣል፣ እናም ወደ እሳቱ ይወረወራል፤ በድጋሚም መንፈሳዊ ሞት፣ አዎን፣ ሁለተኛ ሞት በእነርሱ ላይ ይመ ጣል፤ ለፅድቅ ከሆኑትም ነገሮችም በሚ መለከት በድጋሚ ይቆረጣሉና።

፲፳፪ ስለዚህ ንስሃ ግቡ፤ ንስሃ ግቡ፣ እነዚ ህን ነገሮች በማወቃችሁ፣ እናም ባለማድ ረጋችሁ ራሳችሁን በእርግማን ስር በማድ ረግ ታሰቃያላችሁና፤ እናም ወደዚህ ሁለ ተኛ ሞትም ራሳችሁን ትጎትቱታላችሁ።

፲፳፫ ነገር ግን እነሆ፣ ስለሌላው ምልክት፣ የሞቱን [k]ምልክት፣ በሚመለከት እንደነ ገርኳችሁ፤ እነሆ በሚሞትበት በዚያ ቀን፣ ፀሐይ [l]ትጨልማለች፣ እናም ለእናንተ ብርሃን አትሰጥም፤ ደግሞ ጨረቃና ከዋ ክብትም ይጨልማሉ፤ እናም ከሞተበት ጊዜም እንኳን ጀምሮ [m]ለሶስት ቀናት፣ ከሞት እስከሚነሳበት ጊዜ ድረስ፣ በዚህ በምድር ላይ ምንም ብርሃን አይኖርም።

፲፳፬ አዎን፣ ነፍሱን አሳልፎ በሚሰጥበት ጊዜ ለብዙ ሰዓታት [n]ነጎድጓድ እንዲሁም መብረቅ ይሆናል፣ እናም ምድር ትንቀ ጠቀጣለችና ትናወጣለች፤ እናም በም ድር ላይ ያሉ ዓለቶች፣ በዚህ ጊዜ ጠጣር እንደነበሩ የምታውቋቸው ወይም አብዛ ኛው ክፍል አንድ ጠጣር የነበሩት፣ ከም ድር በላይ የነበሩትና ከሥር ያሉትም ሁሉ [o]ይሰባበራሉ፤

፲፳፭ አዎን ሁለት ቦታ ይከፈላሉ፤ እናም ከዚህም በኋላ ተጨማደውና ተሰነጣ ጥቀው፣ እናም በምድር ላይ የተሰባበሩ ቁርጥራጮች ሆነው፣ አዎን ከመሬት በላ ይና በታች [p]ይገኛሉ።

፲፳፮ እናም እነሆ፣ ኃይለኛ ነፋስ ይኖራል፣

፲፪ [a] ሞዛያ ፫፡፰፣
፫ ኔፊ ፱፡፲፭፣ ኤተር ፭፡፲።
ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ።
፲፫ [b] የሐዋ. ፲፯፡፴–፴፩።
[c] ት.እና ቃ. ፲፱፡፲፯–፳።
፲፭ [d] ቅ.መ.መ. አዳኝ።
[e] አልማ ፴፪፡፳፫።
ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
፲፯ [f] ቅ.መ.መ. የቤዛነት ዕቅድ።
[g] ቅ.መ.መ. የአዳም እና
የሔዋን ውድቀት።
[h] አልማ ፴፪፡፮–፱።
[i] መ ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ሞት።
፲፯ [j] ቅ.መ.መ. ቤዛ፣ ማዳን፣
ቤዛነት።
፳ [k] ፫ ኔፊ ፳፡፭–፳፩።
[l] ሉቃ. ፳፫፡፴፱።
[m] ሞዛያ ፫፡፲።
፳፭ [n] ፫ ኔፊ ፰፡፮።
[o] ፫ ኔፊ ፲፡፱።
፳፪ [p] ፫ ኔፊ ፳፡፲፳።

እናም ከፍታቸው ትልቅ የሆኑ ተራሮች እን ደሸለቆ ዝቅ ይላሉ፣ አሁን ሸለቆ ተብለው የሚጠሩትም በከፍታቸውም ትልቅ የሆኑ ተራሮች ይሆናሉ።

፳፬ እናም ብዙ አውራ ጎዳናዎች ይሰባበ ራሉም፣ ብዙ [ሀ]ከተሞችም የወደሙ ይሆ ናሉ።

፳፭ እናም ብዙ [ለ]መቃብሮችም ይከፈታ ሉና ሙታኖቻቸውን አሳልፈው ይሰጣሉ፣ ለብዙ ሰዎችም ብዙ የሆኑ ቅዱሳን ይታዩ አቸዋል።

፳፮ እናም እነሆ፣ እንደዚህ [ሐ]መልአኩ ተናግሮኛል፤ ለብዙ ሰዓታትም ነጎድጓድ እንዲሁም መብረቅ እንደሚሆንም ተናግ ሮኛል።

፳፯ እናም እንዲህ አለኝ፥ ነጎድጓዱና መብረቁ እንዲሁም አይሎ ነፋስ እያለ እነ ዚህ ነገሮች ይሆናሉ፤ እናም ለሶስት ቀና ትም ምድር [መ]በጨለማ ትከበባለች።

፳፰ እናም መልአኩ እንዲህ አለኝ፥ [ሠ]እነ ዚህ ምልክቶች እና እነዚህ ድንቅ የሆኑት በምድር ገፅ ላይ ሁሉ እንደሚሆኑ ያምኑ ዘንድ፣ በሰው ልጆች መካከል የማያምኑ በት ምንም ምክንያት እንዳይኖር ከዚህ የበ ለጡ ታላቅ ነገሮችን ለብዙዎቹ ይታያሉ—

፳፱ እናም ይህም የሚያምን ሁሉ እንዲ ድን ነው፣ የማያምነውም ጻድቃዊ [ረ]ፍርድ በእርሱ ላይ እንዲመጣ ነው፤ እናም ደግሞ ከተኮነኑ በራሳቸው ላይ የራሳቸውን ፍርድ ያመጣሉ።

፴ እናም አስታውሱ ወንድሞቼ የሚ ጠፋ ቢኖር የሚጠፋው ለራሱ እንደሆነና፣ ክፋትን የሚሰራም ለራሱ የሚሰራ እንደ ሆነ ከእንግዲህ አስታውሱ፤ እነሆም፣ እና ንተ [ሰ]ነፃ ናችሁ፤ ለራሳችሁ እንድትሰሩ ተፈቅዶላችኋል፤ እነሆ እግዚአብሔርም [ሸ]እውቀትን ሰጥቷችኋል እናም እናንተን ነፃ አድርጓችኋል።

፴፩ እርሱም መልካምን ከመጥፎ [ቀ]ታውቁ ዘንድ እውቀትን ሰጥቷችኋል፤ እናም [በ]ህይ ወትን አለበለዚያም ሞትን ትመርጡም ዘንድ የነጻ ምርጫ ሰጥቷችኋል፤ እናም መልካምን መስራት ትችላላችሁ፣ መል ካም ወደ ሆነውም [ተ]ደግማችሁ ትመለሳ ላችሁ፣ ወይንም መልካም የሆነው ለእና ንተ ይመለስላችኋል፤ ወይም ክፉ መስራት ትችላላችሁ፤ እናም ክፉ የሆነውም ደግሞ ይመለስላችኋል።

ምዕራፍ ፲፭

ጌታ ኔፋውያንን የሚገስጻቸው ስለሚወዳ ቸው ነው—የተለወጡ ላማናውያን በእ ምነታቸው ፅኑ እንዲሁም የማይነቃነቁ ናቸው—ጌታ በኋለኛው ቀናት ለላማና ውያን መሃሪ ይሆናል። በ፯ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንግዲህ፣ የተወደዳችሁ ወን ድሞቼ፣ እነሆ፣ ንስሃ ካልገባችሁ ቤታችሁ [ሀ]እንደሚወድምባችሁ እናገራለሁ።

፪ አዎን፣ ንስሃ ካልገባችሁ፣ ሴቶቻችሁ በሚያጠቡበት ቀን የሚያዝኑበት ታላቅ ምክንያት ይኖራቸዋል፤ ምክንያቱም ለመ ሸሽም ትሞክራላችሁ እናም የምትሰደዱ በት ስፍራ አይኖራችሁም፤ አዎን፣ [ለ]እ ርጉዞች ወዮላቸው፣ እነርሱም ከባድ ይሆ ናሉ እናም መሸሽም አይችሉምና፤ ስለዚ ህም ይረገጣሉ እናም እንዲጠፉም ወደኋላ ይቀራሉ።

፫ አዎን፣ የኔፊ ህዝብ ተብለው ለሚጠ ሩት እነዚህን ሁሉ ምልክቶች እናም አስደ ናቂ ነገሮች በሚመለከቱበት ጊዜ ንስሃ ካል ገቡ ወዮላቸው፤ እነሆም፣ በጌታ የተመ

፳፬ [ሀ] ፲ ኔፊ ፱፡ ፣–፣፪።
፳፭ [ለ] ማቴ. ፳፯፡ ፱–፴፡
፣ ኔፊ ፳፣፡ ፱–፣፩።
፳፮ [ሐ] አልማ ፣፣፡ ፣፳፯።
፳፯ [መ] ፩ ኔፊ ፣፱፡ ፣፤ ፣ ኔፊ ፳፡ ፣።
፳፰ [ሠ] ፩ ኔፊ ፣፪፡ ፱–፳።
፳፱ [ረ] ቅ.መ.መ. ፍርድ፣ የመጨረሻው።
፴ [ሰ] ፪ ኔፊ ፪፡ ፳፭–፳፱፤ ሙሴ ፯፡ ፶፯። ቅ.መ.መ. ነጻ ምርጫ።
[ሸ] ቅ.መ.መ. እውቀት።
፴፩ [ቀ] ሞሮኒ ፯፡ ፣፯።
[በ] ፪ ኔፊ ፪፡ ፳፰–፳፱፤ አልማ ፣፡ ፳፭–፳፯።
[ተ] ሐ አልማ ፴፭፡ ፣–፰።
፣፣፭ ፩ [ሀ] ማቴ. ፳፣፡ ፴፯–፴፰።
፪ [ለ] ማቴ. ፳፬፡ ፣፱።
፣ [ሐ] ምሳ. ፣፡ ፣፪፤ ዕብ. ፣፪፡ ፭–፣፩፤ ት. እና ቃ. ፶፭፡ ፩።

ረጡ ህዝቦች የነበሩ ናቸውና፤ አዎን፣ የኔፊን ህዝብ ወዷቸዋል እናም ደግሞ [ሀ]ገስጿቸዋል፤ አዎን፣ ስለሚወዳቸው በክፋታቸው ዘመን ቀጥቷቸዋል።

፭ ነገር ግን እነሆ ወንድሞቼ ላማናውያን ስራቸው ያለማቋረጥ ክፉ ስለነበር ጠልቷቸው ነበር፣ እናም ይህም የሆነበት በአባቶቻቸው [ሀ]ወግ ክፋት የተነሳ ነበር። ነገር ግን እነሆ፣ ደህንነት ግን በኔፋውያን ስብከት የተነሳ መጥቶላቸዋል፤ እናም ለዚህም አላማ ጌታ ቀናቸውን [ለ]አርዝሞላቸዋል።

፮ እናም [ሀ]አብዛኞቹ ክፍሎች በተወሰነላቸው ጎዳና እንደሚንቀሳቀሱ ልብ እንድትሉ እፈልጋለሁ፣ በእግዚአብሔርም ፊት በጥንቃቄ ይራመዳሉ፤ እናም በሙሴ ህግ መሰረትም ትዕዛዛቱንና ህግጋቱን እንዲሁም ፍርዱን ያከብራሉ።

፯ አዎን፣ እንዲህ እላችኋለሁ፣ አብዛኞቹ ይህንን ያደርጋሉ፤ እናም የተቀሩት ወንድሞቻቸውን ወደ እውነት ያመጡ ዘንድም ያለማቋረጥ ትጋትን ያደርጋሉ፤ ስለሆነም በየቀኑም ቁጥራቸውን ከፍ የሚያደርጉ ብዙዎች አሉ።

፰ እናም እነሆ፣ እናንተ በእራሳችሁ እንደምታውቁት፣ ምስክር ሆናችሁበታልና፣ ብዙዎች ወደ እውነት እውቀት የመጡት፣ እናም ክፉውንና የረከሰውን የአባቶቻቸውን ወግ ያውቁትና፣ ቅዱሳት መጻሕፍትንም እንዲያምኑ፤ አዎን፣ እምነትና ንስሃም በልባቸው [ሀ]ለውጥን ስለሚያመጣላቸው ስለተፃፉት ወደ ጌታ እምነትና ወደ ንስሃው ወደሚመሩት የነቢያት ቅዱስ ትንቢቶችም የተመሩት ሁሉ—

፱ ስለዚህ፣ ይህንን እንደሚያውቁ የመጡ ሁሉ፣ በእምነታቸውና ነፃ በተደረጉበትም ነገር [ሀ]ፅኑ እናም የማይነቃነቁ መሆናቸውን በእራሳችሁ አውቃችኋል።

፲ እናም ደግሞ የጦር መሳሪያዎቻቸውን [ሀ]እንደቀበሩና፣ በሆነ አጋጣሚ ኃጢያትን እንሰራለን ብለው በመፍራታቸውም መሣሪያዎቻቸውን ለማንሳት እንደሚፈሩ ታውቃላችሁ፤ አዎን፣ ኃጢያትን ለመስራት መፍራታቸውን ለመመልከት ትችላላችሁ—እነሆም፣ በጠላቶቻቸው እንዲረገጡና እንዲገደሉ ይፈቅዳሉ፣ ጎራዴዎቻቸውንም በእነርሱ ላይ አያነሱም፣ እናም ይህ የሆነበት በክርስቶስ ባላቸው እምነት ነው።

፲ እናም እንግዲህ፣ በሚያምኑበት በዚያ ነገር ሲያምኑ፣ የማያወላውሉ በመሆናቸው፣ ምክንያቱም አንዴ በተገለፀላቸው ጊዜ ፅኑ በመሆናቸውም፣ እነሆ ጌታ ይባርካቸዋል፣ እናም ኃጢአተኞች ቢሆኑም ዘመናቸውን ያረዝምላቸዋል—

፲፩ አዎን፣ እምነት አጥተው ቢመነምኑም፣ በአባቶቻችን እንዲሁም ደግሞ በነቢዩ [ሀ]ዜኖስ፣ እንዲሁም በሌሎች ብዙ ነቢያት ወንድሞቻችን ላማናውያን ድጋሚ እውነትን ወደማወቅ [ለ]መመለስን በተመለከተ የተናገሩበት ቀን እስከሚመጣ ድረስ ጊዜ ቀኖቻቸውን ጌታ [ሐ]ያረዝመዋል—

፲፪ አዎን፣ እንዲህ እላችኋለሁ፣ በኋለኞቹ ጊዜያት የጌታ [ሀ]ቃል ኪዳን ለወንድሞቻችን ለላማናውያንም ይቀርባል፤ እናም ብዙ ስቃዮችም የሚመጡባቸው ቢሆንምና፣ በምድር ገፅ ላይም ለመጠለያቸው ሥፍራን ሳያገኙ [ለ]ወዲህና ወዲያ ቢሰደዱም፣ ቢታደኑም፣ ቢመቱም፣ እናም ከሀገር ውጪ ቢባረሩም፤ ጌታ ለእነርሱ [ሐ]መሃሪ ይሆናል።

፲፫ እናም ይህም የሚሆነው ታላቁና እውነተኛው [ሀ]እረኛ ወደሆነው ወደ አዳኛቸው እውቀት ወደሆነው እውነታዊ እውቀት [ለ]እንደሚመጡ፣ እናም ከእርሱ በጎችም ጋር አብረው እንደሚቆጠሩ በተተነበየው መሰረት ነው።

፭ ሀ ቅ.መ.መ. ባህል።
ለ አልማ ፱፥ ፲፮።
፮ ሀ ሔለ. ፲፫፥ ፩።
፯ ሀ ቅ.መ.መ. መቀየር፣
የተቀየረ።
፱ ሀ አልማ ፳፫፥ ፯፤ ፳፯፥ ፳፯፤
፫ ኔፊ ፯፥ ፲፩።
፲ ሀ አልማ ፳፬፥ ፲፯–፲፱።
፲፩ ሀ ሔለ. ፱፥ ፲፱።
ለ ፪ ኔፊ ፴፥ ፭–፱።
ሐ አልማ ፱፥ ፲፮።
፲፪ ሀ ኢኖስ ፩፥ ፲፪–፲፫።
ለ ሞር. ፭፥ ፲፭።
ሐ ፩ ኔፊ ፲፫፥ ፴፩፤
፪ ኔፊ ፲፥ ፲፱–፲፱፤
ያዕቆ. ፫፥ ፭–፮።
፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. መልካሙ እረኛ።
ለ ፫ ኔፊ ፲፮፥ ፲፪።

፲ፀ ስለዚህ እንዲህ እላችኋለሁ፣ ንስሃ ካልገባችሁ ከእናንተ ይልቅ ለእነርሱ ᵐየተ ሻለ ይሆናል።

፲፭ እነሆም፣ ለእናንተ የታዩት ኃያል ስራ ዎች ለእነርሱ፣ አዎን፣ በአባቶቻቸው ወግ አማካይነት እምነት አጥተው ለመነመኑት፣ ᵐየታዩ ቢሆን ኖሮ በድጋሚ እምነት በማጣት እንደማይመነምኑ እራሳችሁ ለመመልከት ትችላላችሁ።

፲፮ ስለዚህ፣ ጌታ እንዲህ አለ፥ ፈፅሞ አላጠፋቸውም፣ ነገር ግን በጥበብ ቀኔ ወደ እኔ እንዲመለሱ አደርጋቸዋለሁ፣ ይላል ጌታ።

፲፯ እናም እንግዲህ እነሆ፣ ጌታ ስለኔ ፋውያን እንዲህ ይላል፥ ንስሃ ካልገቡና፣ እንደፈቃዴም ካላደረጉ፣ ምንም እንኳን ብዙ አስደናቂ ስራዎች በመካከላቸው ብሰ ራም እምነት ስለሌላቸው ፈፅሞ ᵐአጠፋቸ ዋለሁ፣ ይላል ጌታ፤ እናም በእውነት ጌታ ህያው እንደሆነ እነዚህም ነገሮች ይሆናሉ ይላል ጌታ።

ምዕራፍ ፲፮

ሳሙኤልን የሚያምኑ ኔፋውያን በኔፊ ተጠመቁ—ሳሙኤል ንስሃ ባልገቡ ኔፋ ውያን ቀስቶች እንዲሁም ድንጋይ ሊገ ደል አልቻለም—ጥቂቶች ልባቸውን አጠ ጠሩ እናም ሌሎች መላዕክቶችን ተመለ ከቱ—የማያምኑት፣ በክርስቶስ እናም በኢየሩሳሌም ስለመምጣቱ ማመን ትር ጉም የለውም አሉ። ከ፩–፭ ም.ዓ. ገደማ።

፩ እናም እንግዲህ፣ እንዲህ ሆነ በከተማዋ ግንብ ሳሙኤል ላማናዊው ሲናገር ቃሉን ያዳመጡት ብዙዎች ነበሩ። በቃሉ ያመኑ ሁሉ ሄዱና ኔፊን ፈለጉት፤ እናም በመጡና እርሱን ባገኙት ጊዜ፣ በጌታም ለመጠመቅ ፈልገው፣ ኃጢአታቸውን ለእርሱ ተና ዘዙ፣ እናም አልካዱም።

፪ ነገር ግን የሳሙኤልን ቃላት የማያምኑ ሁሉ በእርሱ ተቆጥተው ነበር፤ እናም በግ ንቡም ላይ ድንጋይ ወረወሩበት፣ እናም ደግሞ በግንቡ ላይ ቆሞ ሳለ ቀስቶቻቸውን ወረወሩበት፤ ነገር ግን በድንጋዮቻቸው ሆነ በበቀስቶቻቸው ሊመቱት እስከማይ ችሉ ድረስ የጌታ መንፈስ ከእርሱ ጋር ነበር።

፫ እንግዲህ እርሱን መምታት እንዳልቻሉ በተመለከቱ ጊዜ፣ በኔፊ ለመጠመቅ እስከ ሚሄዱ ድረስ በቃሉ ያመኑ ብዙዎች ነበሩ።

፬ እነሆም፣ ክርስቶስ ᵐበቅርቡ መምጣ ቱን ያውቁ ዘንድ ምልክቶችንና ድንቅ ነገ ሮችን በማሳየት፣ ኔፊ አጥምቋልም፣ ተን ብዮአልም፣ እናም ሰብኳል፤ በመጮህም ንስሃን ለህዝቡ ተናግሯል፤ በህዝቡም መካ ከል ^ተዓምራቶች ሰርቷል—

፭ በቅርቡ ስለሚመጡትም ነገሮች ለእ ነርሱ በመንገር፣ እንዲያምኑ ባለው አላማ ምክንያት በሚመጡበት ጊዜም ቀደም ብለ ውም እንዲያውቁት ተደርጎ እንደነበር እን ዲያውቁ እና እንዲያስታውሱ ዘንድ አሳ ይቶአቸዋል፤ ስለዚህ የሳሙኤልን ቃላት ያመኑት ሁሉ ለመጠመቅ ወደ እርሱ ሄዱ፤ ንስሃ በመግባት፣ እና ኃጢአታቸውንም በመናዘዝ መጥተዋልና።

፮ ነገር ግን ብዙዎቹ የሳሙኤልን ቃላት አያምኑም ነበር፤ ስለዚህ በድንጋይ እን ዲሁም በቀስታቸው እርሱን ለመምታት አለመቻላቸውን በተገነዘቡ ጊዜ፣ ወደ ሻምበሎቻቸው እንዲህ በማለት ጮሁ፥ ይህንን ሰው ውሰዱትና እሰሩት፣ የዲያ ብሎስ መንፈስ አለበትና፤ እናም በውስጡ ባለው የዲያብሎስ ኃይልም በድንጋይም ሆነ በቀስት ልንመታው አልቻልንም፤ ስለዚህ ያዙትና እስሩት፣ እናም ወዲያ ውሰዱት።

፯ እናም እጃቸውን ሊጭኑበት በሄዱ ጊዜም፣ እነሆ፣ እራሱን ከግንቡ ላይ ዘለ ለና፣ ከምድራቸው ሸሸ፤ አዎን ወደ ራሱም ሃገር ሸሸ፣ እናም በራሱ ህዝብ መካከልም መስበክና መተንበይ ጀመረ።

፰ እናም እነሆ፣ ከዚህም በኋላ ኔፋውያን

፲ፀ ᵐ ሔለ. ፯፡ ፰፲ᴾ።
፲፭ ᵐ ማቴ. ፲፩፡ ፰–፰፲ᴾ።
፲፯ ᵐ ሔለ. ፲ᴾ፡ ፮–፲።
፲፮ ᵐ ሔለ. ፲ᴾ፡ ፮–፲ᴾ
ᵐ ᴹ.ᴹ. ተአምራት።

ምንም ስለእርሱ አልሰሙም፤ እናም የህ
ዝቡ ጉዳዮች ይኸው ነበሩ።
፱ እናም በኔፊ ህዝብ ላይ የመሣፍንቱ ሰማ
ንያ ስድስተኛ የንግስና ዘመን ተፈፀመ።
፲ እናም አብዛኞቹ ሰዎችም ከነኩራታቸው
እንዲሁም ኃጢአታቸው እየቀሩ፤ እናም
ጥቂቶቹ ክፍሎች በእግዚአብሔር ፊት በጥ
ንቃቄ እየተራመዱ፣ የመሣፍንቱ ሰማንያ
ሰባተኛ የንግሥና ዘመን ደግሞም እንደዚህ
ተፈፀመ።
፲፩ እናም ደግሞ በመሣፍንቱ ሰማንያ
ስምንተኛ የንግስና ዘመን ሁኔታዎቹ እነ
ዚህ ነበሩ።
፲፪ እናም ነገር ግን በመሣፍንቱ ሰማንያ
ዘጠነኛ ዓመት የንግስና ዘመን በክፋት ይበ
ልጥ ከመጠጠራቸው፣ እናም በይበልጥ
ከእግዚአብሔር ትዕዛዛት ተቃራኒ የሆኑ
ትን በተጨማሪ ከሚሰሩት በስተቀር በሰ
ዎች ጉዳዮች ላይ ትንሽ የሚሆን ለውጥ
አልነበረም።
፲፫ ነገር ግን እንዲህ ሆነ በመሣፍንቱ ዘጠ
ናኛ የንግስና ዘመን፣ ለህዝቡ [ሀ]ታላቅ ምልክ
ቶች፣ እና ድንቆች፣ ተሰጥተዋቸው ነበር፤
እናም የነቢያቱ ቃላትም መፈፀም [ለ]ጀም
ረው ነበር።
፲፬ እናም [ሐ]መላዕክት ለሰዎች ጠቢብ ለሆኑ
ሰዎችም ታዩአቸው፣ እናም እነርሱ የታ
ላቁ ደስታ የምስራችን ነገሩአቸው፤ በዚ
ህም ዓመት የቅዱሳት መጻሕፍት ትንቢቶ
ችም እንዲህ መፈፀም ጀመሩ።
፲፭ ይሁን እንጂ፣ ኔፋውያንና ደግሞ
ላማናውያን ከሆኑት፣ ከሁሉም በላይ ከሚ
ያምኑት በቀር ሰዎች ልባቸውን ማጠጠር
ጀመሩ፤ እናም በጉልበታቸውና [መ]በጥበባ
ቸው እንዲህ በማለት መመካትም ጀመሩ፥
፲፮ ከብዙዎች መካከል ጥቂት ነገሮችን
በትክክል ገምተዋል፤ ነገር ግን እነሆ፣
የተነገሩት እነዚህ ታላቅ እንዲሁም ድንቅ
ስራዎች ሁሉ እንደማይመጡ እናውቃለን።
፲፯ እናም ምክንያት በማቅረብምና እርስ
በእርሳቸው እንዲህ በማለት መጣላት
ጀመሩ፥
፲፰ እንዲህ ያለ ክርስቶስ የሚባል ፍጡር
ይመጣል ማለት [ሠ]ተገቢ አይደለም፤ ይህም
ከሆነ፣ እናም እርሱም የእግዚአብሔር
ልጅ፣ እንደተባለውም የሰማይና የምድር
አባት ከሆነ በኢየሩሳሌም ላሉት እንደሚ
ያደርገው ለምን እራሱን ለእኛም አይገል
ፅም?
፲፱ አዎን፣ በኢየሩሳሌም ምድር እንደ
ሚያደርገው እራሱን ለምን በዚህች ምድ
ርም አያሳይም?
፳ ነገር ግን እነሆ፣ ይህ በእኛ መካከል ሳይ
ሆን ነገር ግን ራቅ ባለ ምድር፣ በማናውቀው
ምድር በሚመጣው ታላቅ እና አስገራሚ
ነገር እንድናምን የሚያደርግ በአባቶቻችን
የተላለፈልን ክፉ [መ]ወግ እንደሆነ እናውቃ
ለን፤ ስለዚህ እውነት መሆናቸውን በዓይ
ናችን [ረ]ለመመስከር ስለማንችል፣ ባለማወቅ
እንድንቆይ ማድረግ ይችላሉ።
፳፩ እናም ቃልን እንዲያስተምሩን በእ
ነርሱ ስለምንመካ፣ በጮሌነትና፣ በክፉው
ሚስጥራዊ ጥበብ፣ እኛን ለቃላቶቻቸው
አገልጋዮች እንድንሆንና፣ እንድናገለግላ
ቸው ዝቅ አድርጎ የሚያስቆየን፣ እኛ ልን
ረዳው የማንችለውን ታላቅ ሚስጥር ይሰ
ራሉ፤ እናም በህይወት ዘመናችን ሁሉ እራ
ሳችንን ለእነርሱ አሳልፈን ከሰጠን እንደዚህ
በድንቁርና ያቆዩናል።
፳፪ እናም ህዝቦች የማይረቡና [ሸ]ከንቱ በሆ
ኑት ልባቸው ከዚህ የበለጡ ብዙ ነገሮችን
ገመቱ፤ እናም ሰይጣን ያለማቋረጥ ክፋት
እንዲሰሩ ስለሚበጠብጣቸው ይበልጥ ተረ
ብሸው ነበር፤ አዎን፣ እርሱም መልካም
በነበሩት እና በሚመጣው ላይ ልባቸውን
ያጠጥሩ ዘንድ አሉባልታንና፣ ፀብን በም
ድሪቱ ገፅ ሁሉ ላይ ለማሰራጨት ሄዷል።
፳፫ እናም በጌታ ህዝቦች መካከል ምል

[ሀ] ሆ ፲ ኔፊ ፩፡፱።
[ለ] ሔለ. ፲፭፡፲–፲፯።
[ሐ] ሆ አልማ ፲፣፡፳፯።
[መ] ሆ ኢሳ. ፭፡፳፭።
[ሠ] ሆ አልማ ፴፡፲፪–፲፣።
[ረ] ሆ ቅ.መ.መ. ባህል።
[ሸ] ሆ ኤተር ፲፪፡፭–፮፣ ፲፱።
[ቀ] ሆ ቅ.መ.መ. ከንቱ፣ ከንቱነት።

ክቶችና አስገራሚ ስራዎች ቢከናወኑም፣ እናም ብዙ አስደናቂ ነገሮችን ቢያደርጉም፣ ሰይጣን በምድር ገፅ ላይ ሁሉ ባሉ የሰዎች ልብ ታላቅ ሥፍራን ይዟል።

፳፬ እናም በኔፊ ህዝብ ላይ የመሣፍንቱ ዘጠናኛው የንግሥ ዘመን እንደዚህ ተፈ ፀመ።

፳፭ እናም በሔለማንና በወንድ ልጆቹ ዘገባ መሰረት የሔለማን መጽሐፍ እንዲህ ተጠናቀቀ።

ሦስተኛው ኔፊ
የኔፊ መፅሐፍ

የሔለማን ልጅ የነበረው የኔፊ ልጅ

እናም ሔለማን፤ የአልማ ልጅ የነበረው፣ የአልማ ልጅ በሴዴቅያስ የመጀመሪያ የንግስ ዘመን የይሁዳ ንጉስ የነበረው ከኢየሩሳሌም የወጣው፣ የኔፊ ዘርያ የነበረውና የሌሂ ልጅ የነበረው፤ የሔለማን ልጅ ነበር።

ምዕራፍ ፩

የሔለማን ልጅ፣ ኔፊ፣ ከምድሪቱ ሄደ፤ እናም የእርሱ ልጅ ኔፊ መዛግብቱን ጠበቃ ቸው—ምልክቶች እንደዚሁም ድንቅ ነገ ሮች ብዙ ቢሆንም ኃጢአተኞች ፃድቃንን ለመግደል አቀዱ—የክርስቶስ መወለጃ ምሽትም ደረሰ—ምልክቱ ተሰጠ፣ እናም አዲስ ኮከብ ታየች—ውሸትና ማጭበር በር ተስፋፋ፣ እናም የጋድያንቶን ዘራፊ ዎች ብዙዎችን ገደሉ። ፩–፴ ዓ.ም. ገደማ።

እናም እንዲህ ሆነ ዘጠና አንደኛው ዓመት አለፈና ሌሂ ኢየሩሳሌምን ለቀ ከወጣ [ሀ]ስድስት መቶ ዓመት ሆኖ ነበር፤ እናም ይኸውም ላኮኔዎስ በምድሪቱ ላይ ዋና ዳኛ የሆነበት ዓመት ነበር።

፪ እናም የሔለማን ልጅ ኔፊ፣ [ሀ]የነሀስ ሠሌዳዎቹን በተመለከተና የተፃፉትን መዛግብት በሙሉ፣ እናም ሌሂ ኢየሩሳሌምን ለቀ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በቅድ ስና የተቀመጡትን ነገሮች በሙሉ በተመ ለከተ ለታላቁ ልጁ [ለ]ለኔፊ ኃላፊነትን ሰጥ ቶት ከዛራሔምላ ምድር ሄደ።

፫ ከዚያም ከምድሪቱ ተለይቶ ሄደ፣ እናም [ሀ]የሔደበትን ስፍራ ማንም አያውቅም ነበር፤ እናም ልጁ ኔፊ መዛግብቶቹን፣ አዎን፣ የዚህን ህዝብ መዝገብ በእርሱ ምትክ ሆኖ አስቀመጠ።

፬ እናም እንዲህ ሆነ በዘጠና ሁለተኛው ዓመት መጀመሪያ፣ እነሆ፣ የነቢያቱ ትን ቢት ይበልጥ በሙላት መፈፀም ጀመረ፤ በህዝቡ መካከል ታላላቅ ምልክቶች እናም ታላላቅ ተዓምራቶች መሆን ጀምረዋልና።

፭ ነገር ግን በላማናዊው ሳሙኤል [ሀ]የተነ ገሩት ቃላት የተፈፀሙበት ጊዜው አልፎ አል ሲሉ ጥቂቶች መናገር ጀምረው ነበር።

፮ እናም በወንድሞቻቸው ሁኔታም በመ ደሰት እንዲህ ማለት ጀመሩ፥ እነሆ ጊዜው አልፎአልና የሳሙኤልም ቃላት አልተፈጸ ሙም፤ ስለዚህ፣ እናም ይህን ነገር በተመ ለከተ ደስታችሁና እምነታችሁ ከንቱ ነው።

፯ እናም እንዲህ ሆነ እነርሱም በምድሪቱ ላይ ታላቅ ረብሻ አደረጉ፤ እናም የተነገሩት ነገሮች እንደማይፈጸሙ በመፍራት ያመ ኑት ሰዎች እጅግ ማዘን ጀመሩ።

፰ ነገር ግን እነሆ፣ እምነታቸው ከንቱ

፩ ፩ሀ ፪ ኔፊ ፳፭፥፲፱።
፪ሀ አልማ ፴፯፥፫–፭።
ለ ቅ.መ.መ. ኔፊ፣ የኔፊ ልጅ፣ የሔለማን ልጅ።
፫ሀ ፫ ኔፊ ፪፥፱።
፭ሀ ሔለ. ፲፬፥፪–፬።

አለመሆኑን ያውቁ ዘንድ ያንን ቀንና ያንን ምሽት፣ እናም ምንም ምሽት የሌለበትን እንደ አንድ ቀን የሚመስለው ቀን የሚሆ ንበትን በጽናት ጠበቁ።

፱ እንግዲህ እንዲህ ሆነ በነቢዩ ሳሙኤል የተሰጠው ምልክት ካልተፈፀመ በስተቀር ሁሉም በነዚያ ወጎች የሚያምኑት ᵐእንዲ ሞቱ የሚደረግበት በማያምኑት የተመረጠ አንድ ቀን ነበረ።

፲ እናም እንዲህ ሆነ የኔፊ ልጅ፣ ኔፊ፣ ይህንን የህዝቡን ክፋት በተመለከተ ጊዜ፣ ልቡ እጅግ አዝኖ ነበር።

፲፩ እናም እንዲህ ሆነ እርሱም ሄደና በም ድሪቱ ላይም ወደቀ፣ እናም ወደ አምላኩ ለህዝቡ፣ አዎን፣ በአባቶቻቸው ወግ ላይ ባላቸው እምነት የተነሳ ሊጠፉ ለተቃረቡት ድገፋ በኃይል ጮኸ።

፲፪ እናም እንዲህ ሆነ ᵐቀኑን በሙሉ ወደ ጌታ በኃይል ጮኸ፤ እናም እነሆ የጌታ ድምፅ እንዲህ ሲል ወደ እርሱ መጣ፥

፲፫ ራስህን አቅና፤ እናም ተደሰት፤ እነ ሆም፣ ጊዜው ቀርቧልና፣ በዚህች ምሽትም ምልክት ይሰጣል፣ እናም ᵐበሚቀጥለውም ቀን በቅዱሳን ነቢያቶቼ አንደበት ᵃእንዲ ነገሩ ያደረግሁአቸውን በሙሉ እንደሚፈ ጸሙ ለዓለም ለማሳየት ወደ ዓለም እመ ጣለሁ።

፲፬ እነሆ፣ ᵐከዓለም መፈጠር ጀምሮ ለሰው ልጆች እንዲያውቋቸው ያደረኳቸ ውን ነገሮች በሙሉ ᵃለመፈጸም፣ እናም ᵐየአብንና፣ የወልድን ፈቃድ፣ የአብን ፈቃድ በእኔም አማካኝነት፣ እናም የወል ድን በስጋዬም አማካኝነ ለመፈጸም ᵐእመ ጣለሁ። እናም እነሆ፣ ጊዜው ተቃርቧል፤ በዚህች ምሽትም ምልክቱ ይሰጣል።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ ለኔፊ የተነገሩት ቃላት እንደተነገሩት ተፈጸሙ፤ እነሆም፣ ፀሀይ በምትጠልቅበት ጊዜ ጨለማ አልነ በረም፤ እናም ምሽት በሆነም ጊዜ ᵐጨለማ ባለመኖሩ ሰዎች መገረም ጀምሩ።

፲፮ እናም የነቢያቱን ቃላት የማያምኑ፤ በመሬት ላይ ᵐየወደቁ እናም የሞቱ የሚ መስሉ ብዙዎች ነበሩ፤ ምክንያቱም ታላቁ ᵃየጥፋት ዕቅድ በነቢያቱ ቃላት ለሚያም ኑት የተወጠነው እንዳልተሳካ ያውቃሉና፤ ተሰጥቶ የነበረው ምልክት ቀድሞውኑ ቀር ቦአልና።

፲፯ እናም የእግዚአብሔር ልጅ በአጭር ጊዜ እንደሚታይ ማወቅ ጀመሩ፤ አዎን በአጠቃላይ በምድር ገጽ ላይ ያሉት፤ ከምዕራብ እስከ ምስራቅ፤ በምድሪቱ በስ ተሰሜን እስከደቡብ ያሉት ሰዎች በሙሉ ወደ መሬት እስከሚወድቁም ድረስ እጅግ ተደንቀው ነበር።

፲፰ ነቢያቶቹ ስለ እነዚህ ነገሮች ለብዙ ዓመታት መመስከራቸውን፣ እናም የተ ሰጣቸውም ምልክት መድረሱን አውቀዋ ልና፤ እናም በክፋታቸውና ባለማመናቸው ምክንያት መፍራት ጀመሩ።

፲፱ እናም እንዲህ ሆነ በዚያን ምሽት በሙሉ ምንም ጨለማ አልነበረም፣ ነገር ግን እንደ እኩለ ቀን ብርሃን ነበር። እናም እንዲህ ሆነ በትክክለኛው ስርዓት መሰረት፣ በጠዋቱ በድጋሚ ፀሀይ ወጣችና፣ በተሰ ጠው ምልክትም የተነሳ ቀኑም ጌታ ᵐየሚ ወለድበት መሆኑን አውቀው ነበር።

፳ እናም እንዲህ ሆነ፣ አዎን፣ ሁሉም ነገ ሮች፣ እያንዳንዱም በነቢያቱ ቃላት መሰ ረት ነበሩ።

፳፩ እናም እንዲህ ሆነ ደግሞም እንደቃሉ አዲስ ᵐኮከብ ታየ።

፳፪ እናም እንዲህ ሆነ ከዚህ ጊዜ በኋላ ልባቸውን እንዲያጠጥር፤ በታዩትም ምል ክቶች እንዲሁም አስገራሚ ነገሮች እንዳያ

፱ ሀ ቅ.መ.መ. ሰማዕት፣ ሰማዕትነት።
፲፪ ሀ ኢኖስ ፩፡፱፣ ኦ፣ አልማ ፭፡ ፴፯።
፲፫ ሀ ሉቃ. ፪፡ ፲–፲፩።
ለ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—ስለኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ እና ሞት ትንቢቶች።
፲፬ ሀ አልማ ፴፪፡ ፳፯።
ለ ማቴ. ፭፡ ፲፯–፲፰።
ሐ ት.እና ቃ. ፶፫፡ ፫–፱።
መ ዮሐ. ፩፡ ፲፩።
፲፭ ሀ ሔለ. ፲፬፡ ፫።
፲፮ ሀ ሔለ. ፲፬፡ ፯።
ለ ፫ ኔፊ ፩፡ ፱።
፲፱ ሀ ሉቃ. ፪፡ ፩–፯።
፳፩ ሀ ማቴ. ፪፡ ፩–፪፣ ሔለ. ፲፬፡ ፭።

ምኑ በሰይጣን አማካኝነት በሰዎች መካከል ውሸት መሰራጨት ጀመረ፤ ነገር ግን እነዚህ ውሸቶችና ማጭበበር ቢኖሩም አብዛኞቹ ማመን ጀመሩ፣ እናም ወደ ጌታ ተለወጡ።

፳፫ እናም እንዲህ ሆነ ኔፊና፣ ብዙ ሌሎች፣ በሰዎቹ መካከል ᵛለኃጢያት ታላቅ ስርየት ወደሚገኝበት ንስሃ ለማጥ መቅ ሔደ። እናም ሰዎቹ በድጋሚ በምድ ሪቱ ሠላምን ማግኘት ጀመሩ።

፳፬ እናም ጥቂቶች የሙሴን ህግጋት ማክ በር አስፈላጊ ᵛአለመሆኑን በቅዱሳን መጻህ ፍት ለማረጋገጥ በመስበክ ጥረት ከሚያደ ርጉት በስተቀር ፀብ አልነበረም። እንግዲህ በዚህ ነገርም ቅዱሳን መጽሐፍትን ባለመረ ዳታቸው ስህተትን ፈጽመው ነበር።

፳፭ ነገር ግን እንዲህ ሆነ በአፋጣኝ ተለ ወጡ፣ እናም የነበሩትንም ስህተቶች እን ዲያውቁ ተደርገው ነበር፤ ምክንያቱም ህጉ ገና ᵛአለመፈጸሙ፤ እናም በማንኛ ውም ሁኔታም ሁሉም መፈፀም እንደሚገ ባቸው እንዲያውቁት ተደርገዋል፤ አዎን፣ ይህም መፈፀም እንዳለበት ቃል ወደ እነ ርሱ መጣ፤ አዎን፣ ሁሉም እስከሚፈፀም አንዲት ነጥብ ወይም ምልክት አታልፍም፤ ስለዚህ በዚሁ ዓመት ስህተታቸውን እንዲ ያውቁ ተደርገው ነበር፣ እናም ጥፋታቸ ውን ᶮተናዘዙ።

፳፮ እናም የሁሉም ቅዱሳን ነቢያት የትን ቢት ቃላት መሰረት የተሰጡት ምልክቶች በመፈፀም የተነሳ ዘጠና ሁለተኛው ዓመት ምስራች ለህዝቡ አምጥቶ አለፈ።

፳፯ እናም እንዲህ ሆነ በተራራ ከሚኖ ሩት፣ ምድርን ከወረሩት፣ ይዞታቸውና የሚስጥር ቦታቸው በጣም ጠንካራ ሆኑ ሰዎች ሊያሸንፏቸው ከማይችሉት ᵛየጋድ ያንቶን ዘራፊዎች በስተቀር ዘጠና ሶስተኛው ዓመት በሰላም ዓለፈ፣ ስለዚህ በርካታ ግድ ያዎች እናም በህዝቡ ውስጥ ብዙ ግድያዎ ችን ፈጸሙ፤

፳፰ እናም እንዲህ ሆነ ወደ እነርሱ የሸሹ ብዙ ኔፋውያን ተቃዋሚዎች በመኖራ ቸው፤ እነርሱም በምድሪቱ በቀሩት ኔፋ ውያን ላይ ታላቅ ሀዘን እንዲሆን ባደረጉት ምክንያት በዘጠና አራተኛው ዓመት በታ ላቅ መጠን መጨመር ጀመሩ።

፳፱ እናም ደግሞ በላማናውያን መካ ከል የታላቁ ሀዘን መንስኤ ነበር፤ እነ ሆም፣ የደረሱ እናም ዕድሜአቸው የጨ መረ ብዙ ልጆች ነበሩአቸውና እናም ራሳ ቸውን ቻሉና፣ ከጋድያንቶን ዘራፊዎች ጋር እንዲቀላቀሉ ᵛዞራማዊ በነበሩ በጥቂቶች በውሸታቸው እንዲሁም በሸንጋዩ ቃላቶ ቻቸው ተመርተው ነበርና።

፴ እናም ደግሞ ላማናውያን እንደዚህ ተሰቃዩ፣ እናም በሚያድገው ትውልድ ኃጢያት የተነሳም እምነታቸውና ፅድቃ ቸው መመናመን ጀመረ።

ምዕርፍ ፪

ክፋትና እርኩሰት በህዝቡ መካከል ተስፋፉ—ኔፋውያን እና ላማናው ያን ከጋድያንቶን ዘራፊዎች እራሳቸውን ለመከላከል ተዋሃዱ—የተለወጡ ላማና ውያን ነጭ ሆኑ እናም ኔፋውያን ተብለው ተጠሩ። ፭–፲፮ ዓ.ም. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ ደግሞም ዘጠና አምስተኛው ዓመት እንደዚህ አለፈ፣ እናም ሰዎቹ እነዚያን ምልክቶችና የሰሟቸውን አስገራሚ ነገሮች መርሳት ጀመሩ፣ እናም ከሰማይ በሆነው ምልክት ወይም አስገራሚ ነገር መደነቃቸው መቀነስ ጀመሩ፤ በዚህም ልባቸው መደንደንና አዕምሮአቸው መታ ወር ጀመረ፣ እናም ያዩአቸውንና የተመለ ከቱአቸውን በሙሉ አለማመን ጀመሩ—

፪ የሰዎችን ልብ ለመምራትና ᵛለማጭበ ርበር በሰው እንዲሁም በዲያብሎስ ኃይል በተሰሩት በማለት በልባቸው ጥቂት ከንቱ

ᶮ ፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ስርየት።
ᵛ ፲፬ ሀ አልማ ፴፬፡ ፲፫።
ᵛ ፲፭ ሀ ማቴ. ፭፡ ፲፯–፲፰።
ᵛ ፲፮ ሀ ቅ.መ.መ. የጋድያንቶን ዘራፊዎች።
ᵛ ፲፯ ሀ አልማ ፴፡ ፲፭–፲፮።
ᵛ ፲፱ ሀ አልማ ፴፡ ፲፱–፳፡ ᵛ ፪ ሀ ቅ.መ.መ. ሽንገላ (ውሸት)፣ መዋሸት፣ ማታለል።

ነገር አሰላሰሉ፤ እንደዚህም ሰይጣን የሰዎ
ችን ልብ በድጋሚ የራሱ አድርጓል፣ በዚ
ህም የተነሳ አሳውሮአቸዋልና የክርስቶስን
ትምህርት በተመለከተ የሞኝ እናም ከንቱ
ነገር መሆኑን እንዲያምኑ መርቷቸዋል።

፫ እናም እንዲህ ሆነ ሰዎቹ በክፋቶቻቸ
ውና በእርኩሰቶቻቸው መበርታት ጀመሩ፤
እናም ከእንግዲህ ምልክቶችም ሆኑ አስ
ገራሚ ነገሮች እንደሚሰጡ አላመኑም፤
እናም ሰይጣን የሰዎችን ልብ መምራት፣
መፈተንና በምድሪቱ ታላቅ ክፋትን እን
ዲሰሩ ማድረግ [a]ቀጠለ።

፬ እናም ዘጠና ስድስተኛው ዓመት፤
ደግሞም ዘጠና ሰባተኛው ዓመት፤ እናም
ደግሞ ዘጠና ስምንተኛው ዓመት፣ እንዲ
ሁም ደግሞ ዘጠና ዘጠነኛው ዓመት እንደ
ዚህ አለፉ፤

፭ እናም ደግሞ በኔፊ ህዝብ ላይ ንጉስ
ከነበረው [b]ሞዛያ ጊዜ ጀምሮ መቶ ዓመት
አለፈ።

፮ እናም ሌሂ ኢየሩሳሌምን ለቆ ከወጣ
ስድስት መቶ ዘጠኝ ዓመታት አለፉ።

፯ እናም ስለ ክርስቶስ ወደ ዓለም መም
ጣት ለነቢያቱ የተነገሩት ምልክቶች ከተ
ሰጡ ጊዜ አንስቶ ዘጠኝ ዓመታት አለፉ።

፰ እንግዲህ ኔፋውያን ምልክቱ ከተሰጠ
በት ወይንም ከክርስቶስ መምጣት ጀምሮ
ጊዜአቸውን መቁጠር ጀመሩ፤ ስለዚህ
ዘጠኝ ዓመታት አለፉ።

፱ እናም የመዛግብቱ ኃላፊነት የነበረው፣
የኔፊ አባት የነበረው፣ ኔፊ ወደ ዛራሄምላ
ምድር [c]አልተመለሰም፤ እናም በምድሪ
ቱም በሙሉ ሊገኝ አልቻለም።

፲ እናም እንዲህ ሆነ በመካከላቸው ብዙ
ስብከቶች እንዲሁም ትንቢቶች ቢላኩም፣
ህዝቦች በክፋታቸው እንደቆዩ ነበር፤ ደግ
ሞም አስረኛው ዓመት አለፈ፤ እናም
ደግሞ አስራ አንደኛውም ዓመት በክፋታ
ቸው አለፈ።

፲፩ እናም እንዲህ ሆነ በአስራ ሦስተኛው
ዓመት በምድሪቱ ላይ ሁሉ ጦርነቶች እን
ዲሁም ፀብ ተጀመረ፤ የጋድያንቶን ዘራፊ
ዎች እጅግ ብዙ ስለነበሩና፣ ብዙዎችን ስለ
ገደሉ፤ እናም ብዙ ከተሞችንም ስለደመ
ሰሱና፣ በምድሪቱ ላይ ብዙ ግድያና፣ ሞት
ስላሰራጩ፣ ኔፋውያንም ሆኑ ላማናውያን
በእነርሱ ላይ እጃቸውን ለጦርነት ማንሳታ
ቸው አስፈላጊ ነበር።

፲፪ ስለዚህ፣ ወደ ጌታ የተለወጡት ላማና
ውያን በሙሉ ከኔፋውያን ወንድሞቻቸው
ጋር አንድ ሆኑ እናም ለህይወታቸውና ለሴ
ቶቻቸውና ለልጆቻቸው ደህንነት፣ አዎን፣
ደግሞም ልዩ መብቶቻቸውንና የቤተክር
ስቲያናቸውን ክብር እናም አምልኮታቸ
ውንና፣ [d]ነፃነታቸውን እንዲሁም [e]ህልው
ናቸውን እንዲጠብቁ ዘንድ በጋድያንቶን
ዘራፊዎች ላይ መሳሪያዎችን እንዲያነሱ
ተገደው ነበር።

፲፫ እናም እንዲህ ሆነ ከዚህ አስራ ሦስ
ተኛው ዓመት ከማለፉ በፊት ኔፋውያን
በዚህ እጅግ መሪር በሆነው ጦርነት የተ
ነሳ ፈፅመው እንዲጠፉ ማስፈራሪያ ተደ
ርጎባቸው ነበር።

፲፬ እናም እንዲህ ሆነ ከኔፋውያን ጋር
አንድ የሆኑት ላማናውያን ከኔፋውያን ጋር
ተቆጥረው ነበር፤

፲፭ እናም [f]እርግማናቸው ከእነርሱ ተወ
ስዶ ነበር፣ እናም ቆዳቸው እንደኔፋውያን
[g]ነጭ ሆኖ ነበር፤

፲፮ እናም ወጣት ወንዶቻቸው እንዲ
ሁም ሴት ልጆቻቸው እጅግ መልካም ሆኑ፤
እናም ከኔፋውያን ጋር ተቆጠሩና፣ ኔፋው
ያን ተብለው ተጠሩ። እናም አስራ ሶስተ
ኛው ዓመት ተፈፀመ።

፲፯ እናም እንዲህ ሆነ በአስራ አራተኛው
ዓመት መጀመሪያ፣ በዘራፊዎቹ እናም
በኔፊ ህዝብ መካከል የነበረው ጦርነት ቀጠ
ለና፣ እጅግ መሪር ሆነ፤ ይሁን እንጂ፣ የኔፊ

---

a ሀ ት.እና ቃ.፲፡፳፯።
b ሀ ሞዛያ ፳፱፡፴፯–፴፯።
c ሀ ፫ ኔፊ ፭፡፪–፫።
d ሀ ቅ.መ.መ. ነጻ፣ ነጻነት።
ለ ቅ.መ.መ. መብት።
e ሀ አልማ ፲፯፡፲፭፤ ፳፫፡፲፳።
ለ ፪ ኔፊ ፭፡፳፭፤ ፴፡፮፤ ያዕቆ.፫፡፳።
f ሀ ፫ ኔፊ ፪፡፲–፲፭።
g ሀ ሙሴ ፯፡፳–፳፪።

ህዝብ በሌቦቹ ላይ ጥቂት ብልጫ አግኝተው ነበር፣ ስለዚህ ከምድራቸው አስወጥተው ወደ ተራራውና ወደ ሚስጥራዊው ስፍራ ቸው እንዲሸሹ አደረጉአቸው።

፲፰ እናም አስራ አራተኛው ዓመት በዚሁ ተፈፀመ። እናም በአስራ አምስተ ኛው ዓመት በኔፊ ህዝብ ላይ መጡባቸው፤ እናም በኔፊ ሰዎች ክፋትና፣ ፀብና ተቃ ውሞዎች የተነሳ፣ የጋድያንቶን ዘራፊዎች በእነርሱ ላይ ብዙ ብልጫ አገኙ።

፲፱ እናም አስራ አምስተኛው ዓመት በዚሁ ተፈፀመና፣ እንደዚህም ሰዎቹ ብዙ ስቃይ ውስጥ ነበሩ፤ [a]የጥፋት ጎራዴም እነ ርሱን ሊቆርጣቸው እስከሚቃረብ በእነርሱ ላይ ነበር፤ እናም ይህ የሆነው በክፋታቸው የተነሳ ነው።

ምዕራፍ ፫

የጋድያንቶን መሪ፣ ጊድያንሒ፣ ላኮኔዎስ እናም ኔፋውያን እራሳቸውን እንዲሁም ምድራቸውን እንዲያስረክቡ በማስገደድ ጠየቀ—ላኮኔዎስ የወታደሮቹ ዋና ሻምበል አድርጎ ጊድጊዶኒን ሾመው—ኔፋውያን በዛራሄምላ እናም በለጋሱ ምድር እራሳ ቸውን ለመከላከል በአንድነት ተሰበሰቡ። ፲፯–፲፰ ዓ.ም. ገደማ።

፩ እናም እንግዲህ እንዲህ ሆነ ክርስቶስ ከመጣ በአስራ ስድስተኛው ዓመት፣ የም ድሪቱ ገዢ ላኮኔዎስ፣ ከዘራፊዎቹ ቡድን መሪና አስተዳዳሪ ከሆነው ደብዳቤን ተቀ በለ፤ እናም የተፃፉት ቃላት እንዲህ የሚሉ ነበሩ፥

፪ የምድሪቱ ልዑልና ዋና አስተዳዳሪ የሆ ንከው ላኮኔዎስ፤ እነሆ፣ ይህንን ደብዳቤ እጽፍልሃለሁ፤ እናም በጽኑነትህና፣ ደግሞ እናንተ መብታችንና ነፃነታችን ነው ብላ ችሁ የምትገምቱትን በመጠበቅ በህዝብህ ጽኑነት፣ ለአንተ እጅግ ታላቅ የሆነ ምስጋ ናን እሰጥሃለሁ፤ አዎን፣ ነፃነታችሁንና ንብ ረታችሁን እናም ሀገራችሁን ወይም እን ደዚህ የምትጠሯቸውን ለመከላከል በአ ንድ በአምላክ የተረዳችሁ በመምሰል ፀን ታችሁ ቆማችኋል።

፫ እናም ልዑል ላኮኔዎስ፣ ለእኔ የሚያሳ ዝነኝ ቢኖር በእኔ ትዕዛዝ ስር ያሉትን፣ በአ ሁኑ ሰዓት የጦር መሳሪያቸውን ይዘው የቆ ሙትን ብዙ ጀግና ሰዎችን፣ በኔፋውያን ላይ ዝመቱና አጥፋአቸው የሚለውን ቃሉ ንም በታላቅ ጉጉት የሚጠብቁትን ለመቋ ቋም እንደምትችሉ በመገመትህ አንተ ሞኝ እንዲሁም ከንቱ በመሆንህ ያሳዝነኛል።

፬ እናም እርሱንም በጦር ሜዳው በማረጋ ገጤ፣ የማይሸነፈውን መንፈሳቸውን አው ቃለሁ፤ በእነርሱም ላይ ብዙ ስህተቶችን በመፈፀማችሁ በእናንተም ላይ ያለባቸውን ዘላለማዊ ጥላቻ ስለማውቅ፣ ስለዚህ በእ ናንተም ላይ የሚመጡ ከሆነ ፍፁም በሆነ ጥፋት ይጎበኙአችኋል።

፭ ስለዚህ ለደህንነታችሁ በማሰብ፣ ትክ ክል ነው ብላችሁ በምታምኑበት ባላችሁ ፅኑነት እናም በጦር ሜዳው ባላችሁ የጅግ ንነት መንፈስ ምክንያት ይህንን ደብዳቤ ጽፌ በራሴ እጅ አሽጌዋለሁ።

፮ ስለዚህ በጎራዴ ከሚጎበኙአችሁ፤ እናም ጥፋት በእናንተ ላይ ከሚመጣ ለህ ዝቦቼ ከተሞችህን፤ ምድራችሁን እናም ንብረቶችህን እንድትተው በመፈለጌ ይህ ንን ለአንተ ጽፌአለሁ።

፯ ወይንም በሌላ አነጋገር፣ ራሳችሁን ለእኛ ስጡ፣ እናም ከእኛ ጋር አንድ ሁኑና [b]ከሚስጥር ስራዎቻችን ጋር ተባበሩ፤ እናም እንደ እኛም ትሆኑ ዘንድ ወንድሞቻችን ሁኑ፣ አገልጋዮቻችን አትሁኑ፣ ነገር ግን ወንድሞቻችንና የህብቶቻችን ሁሉ አጋር ሁኑ።

፰ እናም እነሆ ይህንን የምታደርጉ ከሆ ናችሁ፣ የማትጠፉ መሆናችሁን [c]በመሃላ አረጋግጥልሃለሁ፤ ነገር ግን ይህንን የማ ታደርጉ ከሆነ፣ በሚቀጥለው ወር ወታ ደሮቼ በአናንተ ላይ እንዲመጡና እጃ ቸውን ባለመመለስ እናም ህይወታችሁን

፲፱ *a* አልማ ፰፡ ፰፱።
ቮ ፯ *b* ሔለ. ፯፡ ፰፪–፰፯።
፰ *c* ኤተር ፰፡ ፲ቮ–፲፱።

እንዳያተርፉ፣ ነገር ግን እንዲገድሉአችሁ
እናም ፈፅሞ እስከምትጠፉ ድረስ ጎራዴ
ዎች በእናንተ ላይ እንዲያርፉ ማዘዜን በመ
ሃላ አረጋግጣለሁ።

፱ እናም እነሆ፣ እኔ ጊድያንሒ ነኝ፤ እናም
የዚህ የጋድያንቶን [ሀ]ሚስጥራዊ ማህበረሰብ
አስተዳዳሪ ነኝ፤ በዚያም ያለው ማህበረሰብ
እንዲሁም ስራዎች [ለ]መልካም መሆናቸውን
አውቃለሁ፤ እናም እነርሱም [ሐ]በጥንት ጊዜ
የነበሩ ናቸውና ለእኛ ተላልፈውልናል።

፲ እናም ላኮኔዎስ፣ ይህንን ደብዳቤ ለአ
ንተ እፅፋለሁ፤ እናም የመንግስታቸውን
መብት ለመንጠቅ በነበረህ ክፋት የተነሳ
ከአንተ የተገነጠሉትን ህዝበቼን መብት፣
እንዲሁም ይህ ህዝቤ መንግስቱንና መብ
ቱን ያለምንም ደም መፋሰስ ይመልስ ዘንድ
ምድርህን እንዲሁም ሀብቶችህን እንደም
ትሰጠኝ ተስፋ አደርጋለሁ፤ እናም ይህንን
ካላደረግህ ስለተነፈጉት ነገሮቻቸው እበቀ
ላለሁ። እኔ ጊድያንሒ ነኝ።

፲፩ እናም እንግዲህ እንዲህ ሆነ ላኮኔዎስ
ይህንን ደብዳቤ በተቀበለበት ጊዜ ጊድ
ያንሒ የኔፋውያንን ምድር በድፍረት በመ
ፈለጉና፣ ደግሞ ህዝቡንም በማስፈራራቱ፣
እናም ወደ ክፋቶቹና፣ ርኩሳኑ ዘራፊዎች
እራሳቸውን በመገንጠል [ሀ]ስህተት ከመስ
ራታቸው በስተቀር ስህተት ያልተቀበሉ
ትን ስህተት እበቀላለሁ በማለቱ እጅግ ተገ
ርሞ ነበር።

፲፪ እናም እነሆ፣ ይህ አስተዳዳሪው፣
ላኮኔዎስ፣ ፃድቅ ሰው ነበር፤ እናም [ሀ]በዘራ
ፊው ፍላጎቶች እንዲሁም ማስፈራራት
ሊፈራ አልቻለም፤ ስለዚህ የዘራፊዎቹ
አስተዳዳሪ የሆነውን የጊድያንሒን ደብ
ዳቤ አላደመጠም፣ ነገር ግን ዘራፊዎቹ ወደ
እነርሱ በሚመጡበት ወቅት ህዝቡም እንዲ
በረቱ ወደ ጌታ እንዲጮህ አደረገ።

፲፫ አዎን፣ ከምድሪቱ በስተቀር ህዝቡም
ሴቶቻቸውን፣ እናም ልጆቻቸውን፣ ከብ
ቶቻቸውንና፣ መንጋዎቻቸውን እንዲሁም
ሀብቶቻቸውን በሙሉ በአንድነት እንዲሰ
በስቡ ዘንድ በመካከላቸው አዋጅን ላከ።

፲፬ እናም በዙሪያቸው ምሽግ እንዲሰ
ራና፣ ጥንካሬአቸውም እጅግ ታላቅ እን
ዲሆን አደረገ። እናም የኔፋውያንና የላማና
ውያን ወታደሮች፣ ወይም ከኔፋውያን መካ
ከል የሚቆጠሩ ሁሉ እነርሱን እንዲጠብቁ፤
በዙሪያቸው ጠባቂ ሆነው እንዲቀመጡ፣
እናም በቀንና በምሽት ከዘራፊዎች እንዲ
ጠብቁአቸው አደረገ።

፲፭ አዎን፣ እንዲህም አላቸው፥ ጌታ
ህያው እንደሆነ፣ ለኃጢአቶቻችሁ ንሰሃ
ካልገባችሁ፣ እናም ወደ ጌታ ካልጮህ
ችሁ በቀር፣ በየትኛውም መንገድ ቢሆን
ከጋድያንቶን ዘራፊዎች አታመልጡም።

፲፮ እናም የላኮኔዎስ ቃላቶች እንዲ
ሁም ትንቢቶች ታላቅ እንዲሁም አስገ
ራሚ በመሆናቸው በህዝቡ ሁሉ ላይ ፍር
ሀት እንዲመጣ አደረገ፤ እናም እንደላኮኔ
ዎስም ቃላት ለማድረግ እራሳቸው በኃይ
ላቸው ጥረት አደረጉ።

፲፯ እናም እንዲህ ሆነ ላኮኔዎስ ዘራፊዎቹ
ከምድረበዳው ወጥተው ወደ እነርሱ በሚ
መጡበት ጊዜ እንዲያዙአቸው በኔፋውያን
ወታደሮች ሁሉ ላይ ዋና ሻምበሎች ሾመ።

፲፰ አሁን ከዋና ሻምበሎች መካከል ዋና
እናም ከኔፋውያን ሠራዊት ሁሉ ታላቁ
አዛዥ የሆነ ተሹሞ ነበር፤ እናም ስሙም
[ሀ]ጊድጊዶኒ ይባል ነበር።

፲፱ እንግዲህ በኔፋውያን ሁሉ መካከል
(ክፋት በሚፈጽሙበት ጊዜ ካልሆነ በስተ
ቀር) የራዕይ እንዲሁም ደግሞ [ሀ]የትንቢት
መንፈስ ያለቸውን ዋና ሻምበሎች የመ
ሾም ባህል ነበር፤ ስለዚህ፣ ይህ ጊድጊዶኒ
በእነርሱ መካከል ታላቅ ነቢይ ነበር፤ ደግ
ሞም ዋና ዳኛም ነበር።

፳ እንግዲህ ህዝቡም ለጊድጊዶኒ እንዲህ
አለው፥ ወደጌታ ፀልይና፣ ዘራፊዎቹን እና

፱ [ሀ] ቅ.መ.መ. የሚስጥር ስብሰባ።
[ለ] አልማ ፴፡ ፶፫።
[ሐ] ሔለ. ፮፡ ፳፮–፴፣ ሙሴ ፭፡ ፳፱፣ ፴፱–፴፪።
፲፩ [ሀ] ሔለ. ፲፬፡ ፴።
፲፪ [ሀ] አልማ ፶፰፡ ፭–፲፩፣ ፫ ኔፊ ፬፡ ፯–፲።
፲፫ [ሀ] ፫ ኔፊ ፮፡ ፮።
፲፱ [ሀ] ቅ.መ.መ. ትንቢት፣ መተንበይ።

ጠቃቸው እናም በራሳቸው ምድር እናጠፋ ቸው ዘንድ ወደ ተራራው እናም ወደ ምድ ረበዳው እንሂድ።

፳፭ ነገር ግን ጊድጊዶኒ እንዲህ አላቸው፡ ጌታ ወደዘራፊዎቹ እንዳንሄድ ᵐይከለክ ላል፤ ወደእነርሱ የምንሄድ ከሆነ ጌታ በእ ጃቸው ᵃእንድንወድቅ ያደርጋል፤ ስለዚህ በምድራችን እምብርት እራሳችንን እና ዘጋጃለን፣ እናም ሠራዊታችንን በሙሉ በአንድ ላይ እንሰበስባለን፣ እናም በእነርሱ ላይ አንሄድም፤ ነገር ግን በእኛ ላይ እስ ከሚመጡ ድረስ እንጠብቃቸዋለን፤ ስለ ዚህ ጌታ ህያው እንደሆነ፣ ይህንን የምና ደርግ ከሆነ እነርሱን በእጃችን ስር እንዲ ወድቁ ያደርጋል።

፳፪ እናም እንዲህ ሆነ በአስራ ሰባተኛው ዓመት፣ በዓመቱ በስተመጨረሻ፣ የላኮኔ ዎስ አዋጅ በምድሪቱ ገፅ ሁሉ ተዳረሰ፤ እናም ፈረሶቻቸውን፣ ሠረገላዎቻቸው ንም፣ የቀንድ ከብቶቻቸውንም፣ እናም መንጋዎቻቸውን ሁሉና፣ ከብቶቻቸውን፣ እህሎቻቸውንም፣ እናም ንብረቶቻቸውን በሙሉ ወሰዱ፣ እናም በሺህዎችና፣ በአ ስር ሺህዎች፣ ከጠላቶቻቸው ለመከላከል ዘንድ አብረው እንዲሰበሰቡ ወደተመደቡላ ቸው ስፍራዎች እስከሚሄዱ ድረስ ዘመቱ።

፳፫ እናም የተመረጠችው ምድር የዛራሄምላ ምድር ነበረች፤ እናም ምድ ሪቱ በዛራሄምላ ምድርና በለጋስ ምድር መካከል ነበረች፤ አዎን፣ በለጋስ ምድርና በወደመው ምድር መካከል ባለው ወሰን።

፳፬ እናም ኔፋውያን ተብለው የሚጠሩ፤ በዚህች ምድር ላይ ራሳቸውን በአንድነት የሰበሰቡ ብዙ ሺህ ሰዎች ነበሩ። እንግዲህ በምድሪቱ ᵐበስተሰሜን በኩል በነበረው ታላቅ እርግማን የተነሳ ላኮኔዎስ በምድሪቱ በስተደቡብ እራሳቸውን በአንድ ላይ እን ዲሰበስቡ አደረገ።

፳፭ እናም ከጠላቶቻቸው እራሳቸውን ሸሸጉ፤ እናም በአንድ ምድርና፣ በአን ድነት ኖሩም፣ በላኮኔዎስ የተነገሩትንም ቃላት ፈሩ፤ በዚህም የተነሳ ለጋጢአቶቻ ቸው በሙሉ ንስሃ ገቡ፤ እናም ጠላቶቻቸው ሊዋጉአቸው በመጡ ጊዜ ᵐእንዲያድናቸው ዘንድ ወደ ጌታ አምላካቸው ፀለዩ።

፳፮ እናም በጠላቶቻቸው የተነሳ እጅግ አዝነው ነበር። እናም ጊድጊዶኒ ከሁሉም ዐይነት የጦር መሳሪያዎችን እንዲሰሩና፣ በትዕዛዙ መሠረት ᵐበጦር መሳሪያ፤ እናም ጋሻና፣ ዘለበት እንዲጠናከሩ አደረገ።

ምዕራፍ ፴

የኔፋውያን ወታደሮች የጋድያንቶን ዘራፊ ዎችን አሸነፉ—ጊድያንሒ ተገደለ፣ እናም ተከታዩ ዜምነሪያህ ተሰቀለ—ኔፋ ውያን ለድላቸው ጌታን አወደሱ። ፲፱–፳፪ ዓ.ም. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ በአስራ ስምንተ ኛው ዓመት መጨረሻ የዘራፊዎቹ ወታ ደሮች ለጦርነት ተዘጋጁ፤ እናም በድንገት ከኮረብታው ላይ ገሰገሱና፣ ከተራራውም፣ ከምድረበዳውና፣ ከጠንካራው ምሽጋ ቸው፣ እንዲሁም ከሚስጢራዊው ስፍራ ዎቻቸው መበታተን ጀመሩ፤ እናም በም ድሪቱ በስተደቡብና በምድሪቱ በስተሰሜን ያለውን ምድር መውሰድ ጀመሩ፤ እናም በኔፋውያን ᵐየተተዉትን ምድሮች በሙ ሉና ባዶ የቀሩትን ከተሞች መያዝ ጀመሩ።

፪ ነገር ግን እነሆ፣ በኔፋውያን ከተተዉት ምድሮች ውስጥ የዱር አውሬዎችም ሆኑ የሚታደኑ የሉም፣ እናም ከምድረበዳው በስተቀር በዘራፊዎቹ የሚታደን ምንም አልነበረም።

፫ እናም ምግብ ስለሚያስፈልጋቸው፣ ዘራፊዎቹ ከምድረበዳው በስተቀር ለመ ኖር አልቻሉም፤ ኔፋውያን ምድራቸውን ባዶ በማድረጋቸው፤ እናም ከብቶቻቸውንና መንጋዎቻቸውንና ሁሉንም ቁሳቁሶቻቸውን በመሰብሰባቸው እነርሱ በአንድነት ነበሩ።

፳፩ ᵃ አልማ ፴፰፡ ፲፩።
ለ ፩ ሳሙ. ፲፭፡ ፲፪።

፳፬ ᵃ አልማ ፳፪፡ ፴፩።
፳፭ ᵃ ቅ.መ.መ. መታመን።

፳፮ ᵃ ፪ ኔፊ ፭፡ ፲፩።
፴ ፩ ᵃ ፲ ኔፊ ፲፡ ፲፣–፲፡ ፳፪።

፬ ስለዚህ፣ ከኔፋውያን ጋር ፊት ለፊት ውጊያ ከመምጣት በስተቀር ዘራፊዎቹ ለመዝረፍ እንዲሁም ምግብን ለማግኘት ዕድል አልነበራቸውም፤ ኔፋውያንም አንድ ነበሩ፤ እናም በቁጥርም እጅግ ብዙ ስለ ነበሩና፣ ቁሳቁሶችንና፣ ፈረሶችን፣ እናም ከብቶችንና፣ ከሁሉም ዐይነት መንጋዎችን በማስቀመጣቸው ለሰባት ዓመታት እንደ ሚያቆያቸው በመዘጋጀት በነዚህም ዓመ ታት ዘራፊዎቹን ከምድረ ገፅ ለማጥፋት ተስፋ አድርገው ነበር፤ እናም አስራ ስም ንተኛው ዓመት እንደዚህ አለፈ።

፭ እናም እንዲህ ሆነ በአስራ ዘጠነኛው ዓመት ጊድያንሒ ከኔፋውያን ጋር ለመ ዋጋት መሄዱ አስፈላጊ መሆኑን አወቀ፤ ምክንያቱም ካልዘረፉና፣ ካልሰረቁ፣ እናም ካልገደሉ በስተቀር በህይወት የሚቆዩበት መንገድ ሊኖር አይችልም ነበር።

፮ እናም ኔፋውያን እንዳይመጡባቸውና እንዳይገድሉአቸው፣ በምድሪቱ ገፅ ላይ እራሳቸውን በመበታተን እህል ሊያመርቱ አልደፈሩም፤ ስለዚህ ጊድያንሒ በዚህ ዓመት ወታደሮቹ ከኔፋውያን ጋር ሄደው እንዲዋጉ ትዕዛዝን ሰጠ።

፯ እናም እንዲህ ሆነ ለውጊያው መጥተው ነበር፤ ይህም በስድስተኛው ወር ነበር፤ እናም እነሆ፣ ለውጊያ የሚመጡበትም ቀን ታላቅ፣ እንዲሁም አስፈሪ ነበር፤ እነርሱም የለበሱት እንደዘራፊዎቹ ነበር፤ እናም በወ ገባቸው ላይ የበግ ቆዳ ታጥቀውና፣ በደም ተነክረው ነበር፣ ራሳቸውንም ተላጭው፣ የራስ ቆብም በላያቸው ላይ ነበራቸው፤ እናም በጦር መሳሪያቸውና በደም በመ ነከራቸው የጊድያንሒ ወታደሮች አቋም ታላቅ እንዲሁም አስፈሪ ነበር።

፰ እናም እንዲህ ሆነ የኔፋውያን ወታደ ሮች የጊድያንሒን ወታደሮች አቋም በተ መለከቱ ጊዜ ሁሉም በመሬት ላይ ወደቁ፣ እናም ጌታ አምላካቸው ያድናቸውና ከጠ ላቶቻቸው እጅ ያሰለቅቃቸው ዘንድ ወደ እርሱ ጮሁ።

፱ እናም እንዲህ ሆነ የጊድያንሒ ወታደ ሮች ይህንን በተመለከቱ ጊዜ ከደስታቸው የተነሳ በሃይል ጮሁ፤ ምክንያቱም ኔፋው ያን ወታደሮቻቸውን በመፍራት ይወድቃሉ ብለው ገምተው ስለነበር ነው።

፲ ነገር ግን በዚህ ነገር ተቆጥተዋል፣ ምክ ንያቱም ኔፋውያን አልፈሩአቸውም ነበ ርና፤ ነገር ግን አምላካቸውን [1]ፈርተው ነበር፣ እናም እንዲጠብቃቸውም ተማፅነ ውት ነበር፤ ስለዚህ የጊድያንሒ ወታደሮች ወደ እነርሱ በሮጡ ጊዜ እነርሱን ለመገና ኘት ተዘጋጅተው ነበር፤ አዎን፣ በጌታም ብርታት ዘራፊዎቹን ተቀበሉአቸው።

፲፩ እናም ጦርነቱ በስድስተኛው ወር ተጀ መረ፤ እናም በዚያ የነበረው ጦርነት ታላቅ እንዲሁም አስፈሪ ነበር፣ አዎን፣ በዚያም የነበረው ግድያ ታላቅ፣ እንዲሁም አስፈሪ ነበር፤ በዚህም የተነሳ ሌሂ ኢየሩሳሌምን ለቆ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በህዝቡ መካከል እንዲህ ያለ ታላቅ ግድያ በጭራሽ አይታ ወቅም ነበር።

፲፪ እናም ጊድያንሒ [2]ማስፈራሪያና መሀላ ቢያደርግም፣ እነሆ፣ ኔፋውያን አሸነፏቸው፣ በዚህም የተነሳ ከፊታቸው ማፈግፈግ ጀመሩ።

፲፫ እናም እንዲህ ሆነ [3]ጊድጊዶኒ ወታ ደሮቹ እስከምድረበዳው ዳርቻ እንዲያሳ ድዱአቸው፤ በእጃቸው የገቡትንም እን ዳይተዉአቸው አዘዘ፤ እናም ወደ ምድ ረበዳው ዳርቻ የጊድጊዶኒ ትዕዛዛት እስ ከሚፈጸሙ ድረስ አሳደዱአቸውና ገደሉ አቸው።

፲፬ እናም እንዲህ ሆነ የቆመውና በድፍ ረት የተዋጋው ጊድያንሒ በሸሸ ጊዜ ተከተ ሉት፤ እጅግ ብርቱ በነበረው ጦርነት በመ ድከሙ ተደረሰበትና ተገደለ። እናም ይህም የዘራፊው ጊድያንሒ መጨረሻ ነበር።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ የኔፋውያን ወታ ደሮች ወደ ደህንነታቸው ስፍራ በድጋሚ ተመለሱ። እናም እንዲህ ሆነ ይህ አስራ ዘጠነኛ ዓመት አለፈ፤ እናም ዘራፊዎቹ

[1] ሀ ቅ.መ.መ. ፍርሀት።
[2] ሀ ፫ ኔፊ ፫፡፩–፲።
[3] ሀ ፫ ኔፊ ፫፡፲፰።

በድጋሚ ለመዋጋት አልመጡም፤ በሀያኛ ውም ዓመት ቢሆን በድጋሚ አልመጡም።

፲፯ እናም በሃያ አንደኛው ዓመት ለውጊያ አልመጡም፤ ነገር ግን በሁሉም አቅጣጫ በኔፊ ህዝብ ዙሪያ ለመክበብ መጡ፤ የኔ ፊን ህዝብ ከምድራቸው ከቆረጡአቸውና በሁሉም አቅጣጫ ከከበቡአቸው፣ እናም ከምሽጉ ውጪ ያሉአቸውን እንቅስቃሴ ዎች በሙሉ ከከለከሉአቸው፣ እንደፍላጎ ቶቻቸው እራሳቸውን ለመስጠት እናስገድ ዳቸዋለን ብለው ገምተው ነበር።

፲፰ እንግዲህ ለራሳቸውም ስሙ ዜምነሪ ያህ የሚባል ሌላ መሪ ሾመው ነበር፤ ስለ ዚህ ይህ ዜምናሪያህ ነው የዚህ ዐይነቱ ከበባ እንዲከናወን ያደረገው።

፲፱ ነገር ግን እነሆ፣ ይህ ለኔፋውያን ጠቃሚ ነበር፤ ምክንያቱም ኔፋውያን በመጋዘናቸው በርካታ ስንቅ በማስቀመ ጣቸው፣ ዘራፊዎቹ ኔፋውያንን በዙሪያቸ ውም በሚገባ ለብቁ ጊዜ በመክበብ ምንም አይነት ጉዳት ለማምጣት አስቸጋሪ ነበርና።

፲፱ እናም በዘራፊዎቹ መካከል በነበረው ስንቅ ትንሽነት፤ እነሆም በህይወት ለመቆ የት በምድረበዳው ውስጥ ካገኙት ሥጋ በስ ተቀር ምንም አልነበራቸውም፤

፳ እናም እንዲህ ሆነ [a]የዱር አደኑ በም ድረበዳው ውስጥ በቂ አልነበረም፤ በዚ ህም የተነሳ ዘራፊዎቹ በረሃብ ሊጠፉ ደር ሰው ነበር።

፳፩ እናም ኔፋውያን ያለማቋረጥ በቀን እንዲሁም በምሽት እየዘመቱና ወታደሮ ቻቸውን ያጠቁና በሺህ እናም በአስር ሺህ የሚቆጠሩትን ይገደሉአቸው ነበር።

፳፪ እናም በቀንና በምሽት በእነርሱ ላይ በሆነው ታላቅ ጥፋትም የተነሳ የዜምነሪያህ ሰዎች ዕቅዳቸውን በመተው ለማፈግፈግ ፈልገው ነበር።

፳፫ እናም እንዲህ ሆነ ዜምነሪያህ ህዝቡ ከተከበቡበት እንዲያፈገፍጉ እንዲሁም በምድሪቱ በሰሜን በኩል ራቅ ወዳለው ስፍራ እንዲዘምቱ አዘዘ።

፳፬ እናም እንግዲህ፣ ጊድጊዶኒ ስለዕቅ ዳቸው በመገንዘቡ፣ እናም ምግብ በመፈለ ጋቸውምና፣ በመካከላቸው በነበረው ታላቅ ግድያ መዳከማቸውን በማወቁ፣ በምሽት ወታደሮቹን ላከና፣ የማፈግፈጊያውን መን ገድም አገደባቸው፤ እናም በሚያፈገፍጉ በት መንገድም ወታደሮቹን አስቀመጠ።

፳፭ እናም ይህንን ያደረጉት በምሽት ነበር፤ እናም ከዘራፊዎቹ አልፈው ተጓዙ፤ ስለዚህ በሚቀጥለውም ቀን ዘራፊዎቹ መን ገዱን በጀመሩበት ጊዜ ከፊለፊት እንዲ ሁም ከጀርባቸው ከኔፋውያን ወታደሮች ጋር ተገናኝተው ነበር።

፳፮ እናም በስተደቡብ የነበሩትም ሌቦች ከማፈግፈጊያው ቦታ መንገዱ ተገድቦባ ቸው ነበር። እናም እነዚህ ነገሮች በሙሉ የተደረጉት በጊድጊዶኒ ትዕዛዝ ነበር።

፳፯ እናም ብዙ ሺህዎች ለኔፋውያን ራሳ ቸውን እስረኛ አድርገው ሰጥተው ነበር፤ እናም ቀሪዎቹም ተገደሉ።

፳፰ እናም መሪአቸው፣ ዜምነሪያህ፣ ተወሰደና በዛፉ ላይ አዎን፣ እስከሚሞት ድረስ በጫፉ ላይ ተሰቀለ። እናም እስ ከሚሞት ድረስ በሰቀሉት ጊዜም ዛፉን መሬት ላይ ጣሉትና፣ እንዲህም ሲሉ በህ ይል ጮሁ፥

፳፱ ይህን ህዝብ በስልጣን እንዲሁም በሚስጥራዊ ሴራዎች የተነሳ እነርሱን ለመ ግደል ለሚፈልጉ፣ ሁሉ፣ ይህ ሰው በመ ሬት ላይ ተቆርጦ እንደተጣለው እነርሱ ንም እንዲቆረጡ ያደርጓቸው ዘንድ ጌታ ህዝቡን በፅድቅ እንዲሁም በልብ ቅድስና ይጠብቃቸው።

፴ እናም ተደሰቱና በድጋሚ በአንድ ድምጽ እንዲህ ሲሉ ጮኹ፥ ይህ ህዝብ [b]የአምላኩን ስም ለጥበቃው እስከጠሩ ድረስ ሁሉ [c]የአብርሃም አምላክ፤ እናም የይስሃቅ አምላክና የያዕቆብ አምላክ በፅድቅ ይጠብ ቃቸው።

፴፩ እናም እንዲህ ሆነ በጠላቶቻቸው እጅ እንዳይወድቁ በመጠበቅ ታላቅ ነገር ስላደ

ረገላቸው ሁሉም በአንድነት መዘመር እን ዲሁም ″አምላካቸውን ማወደስ ጀመሩ።

፴፪ አዎን፣ ″ሆሳዕና ለልዑል እግዚአብ ሔር ብለውም ጮሁ። እናም ልዑል እግ ዚአብሔር፣ [ሀ]ሁሉን የሚገዛው ጌታ እግዚ አብሔር ስሙ የተባረከ ይሁን በማለትም ጮኹ።

፴፫ እናም እግዚአብሔር በታላቅ ቸርነቱ ከጠላቶቻቸው እጅ እንዲወጡ ስላደረጋ ቸው እንባ እስከሚወጣቸው ድረስ ልባቸው በደስታ ተሞልቶ ነበር፤ እናም ከንስሃቸውና ትሁትነታቸው የተነሳ ከዘላለም ጥፋት መዳ ናቸውን ያውቁ ነበር።

ምዕራፍ ፭

ኔፋውያን ንሰሃ ገቡ እናም ኃጢአቶቻቸ ውን ተዉ—ሞርሞን የህዝቡን ታሪክ ፃፈ እናም ዘላለማዊውን ቃል አወጀ—እስራ ኤል ለረጅም ጊዜ ከተበተነበት ይሰበሰ ባል። ፳፪–፳፮ ዓ.ም. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ ቅዱሳን ነቢያት በሙሉ የተናገሩትን ቃላት በጥቂቱም ቢሆን የተጠራጠሩ ከኔፊ ህዝብ መካከል ሀያው ከሆነ ነፍስ አንድም አልነበረም፤ ምክንያ ቱም እነዚህ መፈፀም እንዳለባቸው ያው ቃሉና።

፪ እናም እንደነቢያቱ ቃላት በተሰጡት ብዙ ምልክቶች የተነሳ የክርስቶስ መም ጣት አስፈላጊ መሆኑን ያውቁ ነበር፤ እናም በተከናወኑትም ነገሮች የተነሳ ሁሉም ነገ ሮች በተነገሩት መሰረት መምጣት እንዳለ ባቸውም ያውቁ ነበር።

፫ ስለዚህ እነርሱም ኃጢአቶቻቸውን፣ እንዲሁም እርኩሰቶቻቸውን እንዲሁም ዝሙት መፈጸማቸውን ተዉ፣ እናም ቀንና ምሽት በሙሉ ትጋትም እግዚአብ ሔርን አገለገሉ።

፬ እናም እንግዲህ እንዲህ ሆነ የዘራፊዎ ቹን እስረኞች በሙሉ በመውሰዳቸው በህ ይወት ያመለጠ ምንም ባልነበረበት ጊዜ፣ እስረኞቹንም ወህኒ ቤት ጣሉአቸውና፣ የእ ግዚእብሔር ቃልም እንዲሰበክላቸው አደ ረጉ፤ እናም ለኃጢአታቸው ንስሀ የገቡና ከእንግዲህ ወዲያም ላለመግደል ቃል ኪዳን የሚገቡት ሁሉ ″ተለቀቁ።

፭ ነገር ግን ወደ ቃል ኪዳን ያልገቡ፣ እናም በልባቸው ሚስጥራዊ ግድያውን አሁንም የቀጠሉ፣ አዎን፣ በወንድሞቻ ቸው ላይ ማስፈራሪያ የሚያደርጉ ተፈር ዶባቸዋልና በህጉም መሰረት ተቀጥተዋል።

፮ እናም ብዙ ክፋቶችና ብዙ ግድያዎች የተፈፀሙባቸውን ጥፋቶች፣ እናም ሚስ ጢራዊና እርኩስ ህብረቶችን ሁሉ እንደ ዚህ አቆሙ።

፯ እናም እንደዚህ ″ሃያ ሁለተኛው ዓመት አለፈና፣ ደግሞ ሃያ ሦስተኛው ዓመትም፣ እናም ሃያ አራተኛውና፣ ሃያ አምስተኛው ዓመት እንደዚህ አለፉ።

፰ በጥቂቶች ዐይን ታላቅ እንዲሁም አስ ደናቂ የሆኑ ብዙ ነገሮች ደረሱ፤ ይሁን እንጂ እነዚህ ነገሮች በሙሉ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ሊፃፉ አይቻሉም፤ አዎን፣ ብዛት ባላቸው በእነዚህ ሰዎች መካከል በሃያ አምስት ዓመ ታት ጊዜ የተከናወኑትን ″አንድ መቶኛ እን ኳን ይህ መጽሐፍ ሊይዘው አይችልም፤

፱ ነገር ግን እነሆ የዚህን ህዝብ ታሪኮች በሙሉ የያዙ ″መዛግብቶች አሉ፤ እናም አጭር ነገር ግን እውነት የሆነው ታሪክ ግን በኔፊ ተሰጥቷል።

፲ ስለዚህ የኔፊ ሠሌዳዎች ተብለው በሚ ጠሩት ሠሌዳዎች ላይ በተቀረጹት የኔፊ መዛግብት መሰረት ስለእነዚህ ነገሮች መዛ ግብቱን ፅፌአለሁ።

፲፩ እናም እነሆ፣ ታሪኩን በራሴ እጅ በሠራኋቸው ሠሌዳዎች ላይ እፅፋለሁ።

፴፩ *ሀ* አልማ ፳፮፡፳።
ቅ.መ.መ. አመስጋኝ፣ ምስጋናን፣ ምስጋና መስጠት።

፴፪ *ሀ* ቅ.መ.መ. ሆሳዕና።
ለ ፩ ኔፊ ፩፡፲፬።
ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ።

፭ ፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. መብት።
፲ *ሀ* ፫ ኔፊ ፪፡፳።
፳ *ሀ* ፫ ኔፊ ፳፮፡፮–፲፪።
፱ *ሀ* ሔለ. ፫፡፲፫–፲፭።

፲፪ እናም እነሆ፣ ስሜ ᵐሞርሞን ይባላል፤ የተጠራሁትም አልማ በህዝቡ መካከል ቤተክርስቲያኑን አቋቁሞ በነበረበት፣ አዎን፣ ከመተላለፋቸው በኋላ በመካከላቸው የተቋቋመው የመጀመሪያው ቤተክርስቲያን ባቋቋመበት ᵃበሞርሞን ምድር ስም ነው።

፲፫ እነሆ፣ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዝሙር ነኝ። ዘላለማዊ ህይወትንም ያገኙ ዘንድ፣ በህዝቡ መካከል ቃሉን እንዳሰራጭ በእርሱ ተጠርቻለሁ።

፲፬ እናም ቅዱሳን የነበሩት፤ የሞቱት ፀሎት እንደእምነታቸው በእግዚአብሔር ፈቃድ ይፈጸም ዘንድ፣ የተከናወኑት የእነዚህ ነገሮች ታሪክ ᵇመፃፍ አስፈላጊ ሆኖ ነበር—

፲፭ አዎን ሌሂ ኢየሩሳሌምን ለቆ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን የተከናወነውን በያዘው በአነስተኛው መዝገብ እፅፋለሁ።

፲፮ ስለዚህ የእኔ ጊዜ እስከሚጀመርበት ድረስ ከእኔ በፊት በነበሩት ከተጻፉት ታሪኮች ውስጥ መዛግብቴን እፅፋለሁ፤

፲፯ እናም ከእዚያም በዐይኖቼ የተመለከትኳቸውን ነገሮች ᵇታሪክ ፅፌአለሁ።

፲፰ እናም የፃፍኩትም ታሪክ ትክክለኛ እንዲሁም እውነተኛ መሆናቸውን አውቃለሁኝ፤ ይሁን እንጂ በቋንቋችንም ውሱንነት ምክንያት ᵇልንፅፋቸው የማይቻሉን ብዙ ነገሮች አሉ።

፲፱ እናም አሁን ስለራሴ የምናገረውን አበቃለሁና፣ በፊቴ ስለነበሩት ነገሮች ዘገባዬን እቀጥላለሁ።

፳ እናም እኔ ሞርሞን ነኝና፣ የሌሂ ቀጥተኛ ዘር ነኝ። አባቶቻችንን ከኢየሩሳሌም ምድር በማስወጣቱ (እናም ከምድሪቱ እንዳወጣቸው ከእርሱ ከራሱ በቀር ᵇማንም አያውቅም) እናም ለእኔና ለህዝቤ ለነፍሳችን ደህንነት እውቀትን አብዝቶ ስለሰጠን አምላኬን እንዲሁም አዳኜ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ለማወደስ ምክንያት አለኝ።

፳፩ በእርግጥ ᵐየያዕቆብን ᵃቤት ባርኳል፤ እናም ለዮሴፍም ዘር ᵃመሃሪ ሆኗል።

፳፪ እናም የሌሂ ልጆችም ትዕዛዛቱን እስከጠበቁ ᵇድረስ እንደቃሉም ባርኳቸዋልና እንዲበለፅጉ አድርጓል።

፳፫ አዎን፣ እናም በእርግጥ በድጋሚም የዮሴፍ ዘር ᵇቅሪት የሆኑት ጌታ አምላካቸውን ᵃእንዲያውቁ ያደርጋቸዋል።

፳፬ እናም ጌታ በእርግጥም ህያው እንደሆነ፣ የያዕቆብ ዘር ቅሪት የሆኑትን በሙሉ በምድር ገፅ ላይ ሁሉ የተበተኑትን ከምድር ከአራቱም ማዕዘን ᵇይሰበስባቸዋል።

፳፭ እናም ከያዕቆብ ቤትም ጋር ቃል ኪዳን እንደገባም፣ የያዕቆብ ቤት በሙሉ ከእነርሱ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን ᵇእንዲያውቁ፣ በራሱም ጊዜ ከያዕቆብ ቤት ጋር የገባውን ቃል ኪዳን ያሟላል።

፳፮ እናም የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኛቸውን ᵇያውቃሉ፤ እናም ከተበተኑበት ሥፍራ ከምድር ከአራቱም ማዕዘናት ወደራሳቸው ምድር ይሰበሰባሉ፤ አዎን፣ ጌታም ህያው እንደሆነ ይህም ይሆናል። አሜን።

ምዕራፍ ፮

ኔፋውያን በለፀጉ—ኩራት፤ ሀብት እናም በመደብ መለያየት ተጀመረ—በጥል የተነሳም ቤተክርስቲያኗ ተከፋፈለች—ሰይጣን ሰዎችን በአመጽ መራቸው—ብዙ ነቢያት ስለንሰሃ ጮሁ እናም ተገደሉ—ገዳዮቻቸ

፲፪ ᵃ ሞር. ፩፡፩–፭።
ᵇ ሞዛያ ፲፯፡፬፣ አልማ ፭፡፫።
፲፬ ᵃ ኢኖስ ፩፡፲፫–፲፯፣ ት. እና ቃ. ፣፡፲፱–፳።
፲፯ ᵃ ሞር. ፩፡፩።
፲፰ ᵃ ኤተር ፲፪፡፳፭።
፳ ᵃ ፩ ኔፊ ፱፡፴፯።
፳፩ ᵃ ዘፍጥ. ፴፪፡፳፯።
ᵇ ቅ.መ.መ. እስራኤል።
ሐ ዘዳግ. ፴፣፡፲፣–፲፯።
፳፪ ᵃ ፪ ኔፊ ፩፡፳።
፳፣ ᵃ አልማ ፶፯፡፳፬።
ᵇ ፪ ኔፊ ፣፡፲፪።
፳፬ ᵃ ቅ.መ.መ. እስራኤል—የእስራኤል መሰብሰብ።
፳፭ ᵃ ፣ ኔፊ ፲፯፡፭።
፳፯ ᵃ ፪ ኔፊ ፴፡፭–፰፣ ፣ ኔፊ ፳፡፳፱–፴፱።

ውም የአስተዳደሩን ቦታ ለመያዝ አሴሩ።
፳፤–፴ ዓ.ም. ገደማ።

፩ እናም እንግዲህ እንዲህ ሆነ የኔፊ ህዝብ
እያንዳንዱ፣ ከነቤተሰቡ፣ ከብቶቻቸውና
መንጎቻቸው፣ ፈረሶቻቸውና የቀንድ ከብ
ቶቻቸው እናም የእነርሱ ከሆኑት ሁሉም
ነገሮች ጋር በሃያ ስድስተኛው ዓመት ወደ
ራሳቸው ቦታ ተመለሱ።
፪ እናም እንዲህ ሆነ ስንቃቸውን በሙሉ
አልተመገቡም ነበር፤ ስለዚህ ያልተመገቧ
ቸውን ከሁሉም አይነት እህልና፣ ወርቃ
ቸውን፣ እናም ብራቸውንና፣ የከበሩ ነገ
ሮቻቸውን በሙሉ ወሰዱ፣ እናም ከሰሜ
ንና ከደቡብ፣ ከምድሪቱ በስተሰሜን እን
ዲሁም ከምድሪቱ በስተደቡብ በኩል ወደ
ራሳቸው ምድር እንዲሁም ወደ ይዞታዎ
ቻቸው ተመለሱ።
፫ እናም ላማናውያን ሆነው ለመቅረት
ይፈልጉ የነበሩት፣ የምድሪቱን ሠላም እን
ዲጠብቁ ቃል ኪዳን የገቡት ዘራፊዎች፣
ህይወታቸውን ለማቆየት ይሰሩበት ዘንድ
በቁጥራቸው መጠን መሬት ተሰጣቸው፤
እናም እንደዚህ በምድሪቱ ሁሉ ላይ ሠላ
ምን አሰፈኑ።
፬ እናም በድጋሚ በታላቅ ሁኔታ መበ
ልፀግና መጨመር ጀመሩ፤ እናም ሃያ
ስድስተኛውና ሃያ ሰባተኛው ዓመት አለፈ፤
እናም በምድሪቱ ላይ ታላቅ የሆነ ስምም
ነት ነበር፤ ህግጋታቸውንም በሚዛናዊነትና
በፍትሃዊ ፍርድ መሰረት ሰሩ።
፭ እናም አሁን ህዝቡ ወደመተላለፍ ካል
ወደቁ በስተቀር በምድሪቱ ላይ ሁሉ ያለ
ማቋረጥ ለመበልጸግ የሚከለክላቸው ምንም
ነገር አልነበረም።
፮ እናም እንግዲህ ጊድጊዶኒና፣ ዳኛው
ላኮኔዎስ፣ እናም ተሹመው የነበሩት መሪ
ዎች ነበሩ በምድሪቱ ላይ ይህንን ታላቅ
ሠላም የመሰረቱት።
፯ እናም እንዲህ ሆነ በአዲስ ሁኔታም የተ
ሰሩ ብዙ ከተሞች ነበሩ፤ እናም የታደሱ
ብዙ አሮጌ ከተሞችም ነበሩ።
፰ እናም ብዙ አውራጎዳናዎችም ተሰር
ተው ነበር፤ እናም ከአንዱ ከተማ ወደ ሌላ
ኛው ከተማና፣ ከአንደኛዋ ምድር ወደ ሌላ
ኛዋ፣ እንዲሁም ከስፍራ ስፍራ የሚያመሩ
ብዙ መንገዶች ተሰርተው ነበር።
፱ እናም ሃያ ስምንተኛው ዓመት እንደዚህ
አለፈ፤ እናም ህዝቡ ዘለቄታ ያለው ሠላ
ምን አገኘ።
፲ ነገር ግን በሃያ ዘጠነኛው ዓመት በህዝቡ
መካከል ጥቂት ፀብ ተጀመረ፤ እናም አን
ዳንድ ሰዎችም እጅግ ሀብታም በመሆና
ቸው እስከ ታላቅ ማሳደድም ድረስ "በኩ
ራት እንዲሁም ትዕቢት ተነሳስተው ነበር፤
፲፩ በምድሪቱም ብዙ ነጋዴዎች፣ እናም
ደግሞ ብዙ የህግ አዋቂዎች፣ እናም ብዙ
ሹማምንት ነበሩና።
፲፪ እናም ህዝቡ እንደ "ሀብቱና ለትም
ህርቱ ባለው ዕድል መሰረት በደረጃ መከ
ፋፈል ጀመሩ፤ አዎን፣ አንዳንድ ሰዎች
በድህነታቸው የተነሳ አላዋቂዎች ነበሩ፤
እናም ሌሎች ደግሞ ሀብታሞች በመሆና
ቸው ታላቅ ዕውቀትን ተቀብለዋል።
፲፫ አንዳንድ ሰዎች በኩራት ሲወጠሩ፣
እናም ሌሎች እጅግ ትሁት ነበሩ፤ ሌሎች
ወቀሳን በወቀሳ ሲመልሱ እንዲሁም ሌሎች
"ስደትንና ሁሉንም አይነት ስቃዮች ይቀበሉ
ነበር፣ እናም በድጋሚም "ለመሳደብ አይ
መለሱም፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት
ትሁት እንዲሁም የተጸጸቱ ነበሩ።
፲፬ እናም እንደዚህ በምድሪቱ ሁሉ ታላቅ
ጥፋት መጣ፣ በዚህም የተነሳ በቤተክርስ
ቲያኗ መከፋፈል ተጀመረ፤ አዎን፣ በዚ
ህም የተነሳ በሠላሳኛው ዓመት ወደ እውነ
ተኛው እምነት ተለውጠው ከነበሩት ጥቂት
ላማናውያን መካከል በስተቀር፣ በምድሪቱ
በሙሉ ቤተክርስቲያኗ ተከፋፍላ ነበር፤

፮ ፲ ሀ ቅ.መ.መ. ኩራት።
፲፪ ሀ ፩ ጢሞ. ፮ ፡ ፲፯–፲፱ ፤
ሔለ. ፱ ፡ ፲፪።
፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. ማሳደድ፣
መሳደድ።
ለ ማቴ. ፭ ፡ ፴፱ ፤
፱ ኔፊ ፩ ፡ ፴፬ ፤
ት. እና ቃ. ፲፰ ፡ ፳፫–፳፭።

እናም እነርሱም ፅኑ፤ የማይለወጡ፤ እናም የማይነቃነቁ፣ ባላቸው ᵐትጋት ሁሉ የጌታን ትዕዛዛት ለመጠበቅ ፈቃደኞች በመሆናቸው ከእውነተኛው እምነታቸው አይሸሹም።

፲፭ እንግዲህ የህዝቡ የዚህ ክፋት መንስ ኤው ይህ ነበር—ይህን ህዝብ ሁሉንም ዐይ ነት ክፋት እንዲያደርግ ለማነሳሳት፣ እናም በኩራት እንዲወጣጡ ለማድረግ፤ ኃይል ንና ስልጣንን፣ እናም ሀብትንና የዓለምን ከንቱ ነገሮች እንዲሹ ለመፈተን ሰይጣን ታላቅ ሀይል ነበረው።

፲፮ እናም ሰይጣን የሰዎችን ልብ ሁሉንም ዐይነት ክፋት እንዲሰሩ እንደዚህ መርቷቸ ዋል፤ ስለዚህ በሠላሙ ተደስተዋል፣ ነገር ግን ለጥቂት ዓመታት ብቻ ነበር።

፲፯ እናም በሠላሳኛው ዓመት መጀመ ሪያ—ህዝቡም ዲያብሎስ ሊመራቸው በፈ ለገበት ወደማንኛቸውም ᵐፈተናዎች እንዲ ገቡና፣ የፈለገውን የትኛውን ዐይነት ክፋት እንዲሰሩ ለረጅም ጊዜ ተለቀው ስለነበር፣ እናም በዚህ በሠላሳኛው ዓመት መጀመ ሪያ ላይ እንደዚህ አሰቃቂ በሆነ ኃጢያት ውስጥ ነበሩ።

፲፰ እንግዲህ ᵐባለማወቅ ኃጢያትን አል ሰሩም፤ ምክንያቱም እነርሱን በተመለከተ ተምረው ስለነበሩ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ያውቁት ነበር፤ ስለዚህ ሆን ብለው በእግዚ አብሔር ላይ ᵃአምጸዋል።

፲፱ እናም እንግዲህ ይህ በላኮኔዎስ ልጅ በላኮኔዎስ ዘመን ነበር፣ የላኮኔዎስ ልጅ የአባቱን ወንበር ይዞ እናም ህዝቡን በዚህ አመት ያስተዳደረው ነበርና።

፳ እናም ስለህዝቡ ኃጢያትና ክፋት በምድሪቱ ላይ በህዝቡ መካከል በመቆም በድፍረት በመስበክና በመመስከር እናም ጌታ ለህዝቡ የሚያደርገውን ቤዛነት በሌላ አነጋገር የክርስቶስን ትንሳኤ በተመለከተ ከሰማይ ᵐተነሳስተው የተላኩ ሰዎች ነበሩ።

እናም እርነሱም በድፍረት ᵃስለሞቱና ስለ ስቃዩ መሰከሩ።

፳፩ እንግዲህ ስለነዚህ ነገሮች በመመ ስከራቸው ምክንያት እጅግ የተቆጡ ብዙ ሰዎች ነበሩ፤ እናም ተቆጥተው የነበሩት በአብዛኛው ዋና ዳኞች፣ እናም የካህናት አለቆች፣ እንዲሁም ጠበቃዎች ᵐነበሩ፤ አዎን፣ ጠበቃዎች የነበሩት በሙሉ እነዚ ህን ነገሮች በመሰከሩት ተቆጥተው ነበር።

፳፪ እንግዲህ ቅጣቱም በምድሪቱ ገዢ ካልተፈረመበት በቀር ማንንም በሞት የመ ቅጣት ስልጣን ያላቸው ጠበቃ፣ ዳኛም ሆነ የካህናት አለቃ አልነበሩም።

፳፫ እንግዲህ ክርስቶስን የሚመለከቱ ነገሮችን የመሰከሩ፤ በድፍረት የተናገሩ፣ የመሞታቸው እውቀት ወደ አስተዳዳሪው ከሞቱ በኋላ ብቻ እንዲመጣም በዳኛዎችም በሚስጥር የተገደሉ ብዙዎች ነበሩ።

፳፬ አሁን እነሆ፣ ይህ ማንም ሰው ከምድ ሪቱ አስተዳዳሪ ስልጣን ካልተሰጠው መገ ደል የለበትም ከሚለው ከምድሪቱ ህግጋት ጋር የሚቃረን ነበር—

፳፭ ስለዚህ የጌታን ነቢያት እንዲሞቱ ከህጉ ውጪ በፈረዱባቸው ዳኞች ላይ በዛራሄምላ ምድር ለነበረው አስተዳዳሪ አቤቱታ ቀረበ።

፳፮ እንግዲህ እንዲህ ሆነ እነርሱም ተወ ሰዱ፣ እናም በህዝቡ በተሰጠው ᵐህግ መሰ ረት በሰሩት ወንጀል ላይ እንዲፈረድባቸው በዳኛው ፊት ቀረቡ።

፳፯ እንግዲህ እንዲህ ሆነ እነዚያም ዳኞች ብዙ ጓደኞችና ወገን ነበሩአቸው፤ እናም ቀሪዎቹ አዎን፣ ሁሉም ጠበቆችና፣ የካ ህናት አለቆች፣ እራሳቸውን በአንድነት ሰብስበው እናም በህጉም እንዲፈረድባ ቸው ከቀረቡት ዳኞች ወገኖች ጋር ተቀ ላቅለው ነበር።

፳፰ እናም በአንድነት ወደ ᵐቃል ኪዳኑ፣

፲፩ ᵐ ቅ.መ.መ. ትጋት።
፲፯ ᵐ ቅ.መ.መ. መፈተን፣ ፈተና።
፲፰ ᵐ ሞዛያ ፲፡ ፲፩።
ᵃ ቅ.መ.መ. አመጽ።
፳ ᵐ ቅ.መ.መ. መነሳሻ፣ መነሳሳት፤ ነቢይ።
ᵃ ቅ.መ.መ. መሰቀል፤ የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ።
፳፩ ᵐ ት. እና ቃ. ፱፳፩፡ ፴፯–፴፱። ቅ.መ.መ. ክህደት።
፳፪ ᵐ ሞዛያ ፳፱፡ ፳፭፤ አልማ ፩፡ ፲፩።
፳፫ ᵐ ቅ.መ.መ. የሚስጥር ስብሰባ።

አዎን፣ በጥንት ጊዜ በነበሩት ወደተሰጠው ቃል ኪዳን፣ በጻድቅነት ላይ ለመተባበር [ሀ]በዲያብሎስ ወደተሰጠው እና ወደሚተዳደረው ቃል ኪዳን ገቡ።

፳፱ ስለዚህ እነርሱም በጌታ ሰዎች ላይ በአንድነት ተባበሩ፣ እናም እነርሱንም ለማጥፋትና በህጉ መሰረት ሊፈረድባቸው አጥብቆ ከያዛቸው ከፍትህ በግድያ ጥፋተኛ የነበሩትን ለማዳን ቃል ኪዳን ገብተው ነበር።

፴ እናም ህጉንና የሀገር መብታቸውን ለማስጠበቅ አልተቀበሉም፤ እናም አስተዳዳሪውን ለማጥፋትና ምድሪቱም ከእንግዲህ በነፃነት እንዳትሆን፣ ነገር ግን በንጉስ አገዛዝ ስር እንድትሆን [ሁ]ንጉስ በምድሪቷ ላይ ለመመስረት እርስ በርሳቸው ቃል ኪዳን ገቡ።

ምዕራፍ ፲፩

ዋናው ዳኛ ተገደለ፣ መንግስቱም ጠፋ፣ እናም ህዝቡም በጎሳ ተከፋፈለ—ፀረ ክርስቶስ የሆነው ያዕቆብም የሚስጥራዊው ሴራዎች ንጉስ ሆነ—ኔፊ ንሰሃንና በክርስቶስ እምነትን ሰበከ—መላዕክት ዕለት በዕለት አገለገሉት፣ እናም ወንድሙን ከሞት አስነሳ—ብዙዎች ንሰሃ ገቡ፣ እናም ተጠመቁ። ፴–፴፫ ዓ.ም. ገደማ።

፩ አሁን እነሆ፣ በምድሪቱ ላይ ንጉስ እንዳልመሰረቱ አሳያችኋለሁ፤ ነገር ግን በዚሁ ዓመት፤ አዎን፣ በሰላሳኛው ዓመት፣ በፍርድ ወንበሩ ላይ ጥፋትን አድርሰው ነበር፤ አዎን የምድሪቱንም ዋና ዳኛ ገደሉ።

፪ እናም ህዝቡ እርስ በርስ ተከፋፍሎ ነበር፤ እናም እያንዳንዱ ሰው በቤተሰቡና በነገድና በጓደኞቻቸው በጎሳ ተከፋፍሎ ነበር፤ እንደዚህም የምድሪቱን አስተዳደር አጠፉ።

፫ እናም እያንዳንዱ ጎሳ አለቃ ወይንም መሪ በራሱ ላይ ሾመ፤ እናም እነርሱ ጎሳዎችና የጎሳ መሪዎች ሆኑ።

፬ እንግዲህ እነሆ፣ ብዙ ቤተሰብ እናም ነገድና ጓደኞች ያልነበሩት ማንም ሰው አልነበረም፤ ስለዚህ ጎሳዎቹም እጅግ ታላቅ ሆኑ።

፭ እንግዲህ ይህ ሁሉ ተደረገ፤ እናም እስካሁን በመካከላቸው ጦርነት አልነበረም፤ እናም ለሰይጣን ኃይል እራሳቸውን [ሂ]የሰጡ ስለነበር ይህ ሁሉ ክፋት በህዝቡ ላይ መጥቷል።

፮ እናም ነቢያቱን በገደሉት ጓደኞችና፣ ነገዶች [ሄ]ሚስጢራዊ ሴራዎች የተነሳ የመንግስት ደንቦች ጠፍተው ነበር።

፯ እናም ይበልጥ ፃድቃን የነበሩት ሰዎች ሙሉ በሙሉ ኃጢአተኞች እስከሚሆኑ ድረስ በምድሪቱ ታላቅ ፀብ እንዲሆን አደረጉ፣ አዎን፣ በመካከላቸው ጥቂት ፃድቃኖች ብቻ ነበሩ።

፰ እናም አብዛኞቹም ሰዎች ውሻ ወደ [ሁ]ትፋቱ እንደሚመለስ፣ ደግሞም የታጠበች እሪያ በጭቃ ለመንከባለል እንደምትሄድ በድጋሚ ከፅድቅ ወደ ክፋት ሲዞሩ ስድስተኛው ዓመት አላለፈም ነበር።

፱ እንግዲህ በህዝቡ ላይ ታላቅ ክፋትን ያመጣው ይህ ሚስጥራዊው ሴራ እራሳቸውን በአንድነት ሰበሰቡ፣ እናም ከበላያቸው ያዕቆብ ብለው የሚጠሩትን ሰው አስቀመጡ፤

፲ እናም እርሱን ንጉሳችን ብለው ጠሩት፤ ስለዚህ እርሱም በክፉዎቹ ቡድን ላይ ንጉስ ሆነ፤ እናም እርሱ ስለ ኢየሱስ በመሰከሩት ነቢያት ላይ ድምፅ ከሰጡት ዋና የነበር ነው።

፲፩ እናም እንዲህ ሆነ እያንዳንዱ ህግጋቱን መሪዎቻቸው ከማቋቋሙ በስተቀር በአንድነት እንደተሰበሰቡት የጎሳ ሰዎች አይነት በቁጥር በርካታ አልነበሩም፤ ይሁን እንጂ እርስ በርስ ጠላቶች ነበሩ፤ ምንም እንኳን እነርሱ ፃድቃን ያልነበሩ ቢሆኑም አስተዳ

፳፯ ሀ ሔለ. ፤ ፳፣ ፳–፴።
፴ ሀ ፩ ሳሙ. ፰ ፡ ፭–፯ ፤ አልማ ፶፩ ፡ ፭።
፲ ሀ ፩ ኔፊ ፡ ፲ ፤ ፲ ፡ ፲–፲፯ ፤ አልማ ፲ ፡ ፳፭።
፲፩ ሀ ፩ ኔፊ ፡ ፲ ፤ ፲ ፡ ፲።
፲፭ ሀ ሮሜ ፤ ፲ ፡ ፲–፲፯ ፤ አልማ ፲ ፡ ፳፭።
፲ ሀ ፩ ኔፊ ፡ ፲ ፤ ፲ ፡ ፲።
፲ ሀ ምሳ. ፳፯ ፡ ፲፩ ፤ ፩ ጴጥ. ፪ ፡ ፳፪።

ደሩን ለማጥፋት ወደ ቃል ኪዳኑ ከገቡት ጋር በጥላቻ አንድ ሆነው ነበር።

፲፪ ስለዚህ ያዕቆብ ጠላቶቻቸው ከእነርሱ ይበልጥ ብዙ መሆናቸውን በመመልከቱ፤ የቡድኑ ንጉስ በመሆኑ፤ ህዝቡን በምድሪቱ በስተሰሜን ጫፍ በኩል እንዲሸሹና፣ ከተቃዋሚዎቹም ጋር እስከሚገናኙ ድረስ ለራሳቸው ᵐመንግስት እንዲያቋቁሙ (ብዙ ተቃዋሚዎችም እንዲኖሩ እነርሱን ሸንግሎአቸዋልና) እናም ከጎሳ ህዝብ ጋር ለመጣላት በተገቢው ሁኔታ እንዲጠናከሩ ህዝቡን አዘዘ፤ እናም ይህንንም አደረጉ።

፲፫ እናም ህዝቡን እስከሚያልፉ ድረስ እንዳይታገዱ ጉዞአቸው እጅግ ፈጣን ነበር። እናም ሠላሳኛው ዓመት እንዲህ ተፈፀመ፤ እናም የኔፊ ህዝብ ጉዳይም ይህ ነበር።

፲፬ እናም እንዲህ ሆነ በሠላሳ አንደኛው ዓመት እያንዳንዱ ሰው በቤተሰቡ፤ በነገድና በየጓደኞቹ በጎሳው ተከፋፍሎ ነበር፤ ይሁን እንጂ እርስ በርስ እንዳይዋጉ ስም ምነት ላይ ደርሰው ነበር፤ ነገር ግን አለቆቻቸው እናም መሪዎቻቸው በነበሩት አስተሳሰብ ስለሚመሩ በህግጋት እንዲሁም በመንግስታቸው አንድ አልሆኑም ነበር። ነገር ግን አንደኛው ጎሳ ሌላኛውን እንዳይተላለፍ ጥብቅ ህጎችን አወጡ፤ በዚህም የተነሳ በተወሰነ ደረጃ በምድሪቱ ላይ ሰላም ሆነ፤ ይሁን እንጂ ልባቸው ከጌታ ከአምላካቸው ተመልሶ ነበር፣ እናም ነቢያቶችን በድንጋይ ወግረዋልና ከመካከላቸውም አውጥተው ጥለዋቸዋል።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ ᵐኔፊ—በመላዕክቶችና ደግሞ በጌታ ድምፅ በመጎብኘቱ፤ ስለዚህ መላእክቶችንም በማየቱ፣ እናም የዐይን ምስክር በመሆኑና፣ ስለክርስቶስ አገልግሎት በተመለከተ ያውቅ ዘንድ ሀይል ስለተሰጠው፣ እናም ደግሞ ከፅድቅ ሥራቸው ወደ ክፋትና እርኩሰታቸው በፍጥነት ስለመመለሳቸው የዐይን ምስክር በመሆኑ፤

፲፮ ስለዚህ በልባቸው ጠጣርነት እናም በአዕምሮአቸው መታወር በማዘኑ—በዚያው ዓመት ወደእነርሱ ሄደ፣ እናም በድፍረት ስለንስሃ እንዲሁም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት ለኃጢያት ስርየት እንደሚገኝ መመስከር ጀመረ።

፲፯ እናም ብዙ ነገሮችን ሰበከላቸውና፣ ሁሉም ነገሮች ሊፃፉ አልቻሉም፣ እናም ግማሹን እንኳን ብቁ አይሆኑም፤ ስለዚህ በዚህ መጽሐፍ አልተፃፉም። እናም ኔፊ ᵐበሃይል እንዲሁም በታላቅ ሥልጣን አገለገለ።

፲፰ እናም እንዲህ ሆነ ከእነርሱ የበለጠ ስልጣን ስለነበረው በእርሱ ተቆጥተው ነበር፤ የእርሱን ቃል ላለማመን ᵐአስቸጋሪ ይሆንባቸዋልና፣ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እምነቱ ታላቅ ስለነበር መላእክት በየቀኑ ያገለግሉት ነበርና።

፲፱ እናም በኢየሱስ ስም ዲያብሎስን እንዲሁም ᵐእርኩስ መንፈስን አስወጥቷል፤ እናም በህዝቡ በድንጋይ ከተወገረና በሞት እንዲሰቃይ ከተደረገ በኋላ ወንድሙንም እንኳን ከሞት አስነስቷል።

፳ እነም ህዝቡ ይህን ተመለከቱ፣ እናም ስለዚህም መስክረዋልና፣ በኃይሉም ምክንያት ተቆጥተው ነበር፤ እናም ደግሞ በኢየሱስ ስም በህዝቡ ፊትም ብዙ ᵐተአምራትን አድርጓል።

፳፩ እናም እንዲህ ሆነ ሠላሳ አንደኛው ዓመት አለፈ፣ እናም ወደ ጌታ የተለወጡ ጥቂት ሰዎች ብቻ ነበሩ፤ ነገር ግን ብዙዎች በሚያምኑበት በኢየሱስ ክርስቶስ በነበረው የእግዚአብሔር ኃይልና መንፈስ እንዲሁም ሥልጣን እንደተጎበኙ በእውነት ለህዝቡ አስታውቀዋል።

፳፪ እናም ዲያብሎሶች ከውስጣቸው የወጣላቸውና፣ ከህመማቸውና፣ ከደዌም የዳኑ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ደርሶ በላያቸው ላይ እንደሰራና እንደተፈወሱ ለህዝቡ

፲፪ ᵐ ፫ ኔፊ ፮፡፴።
፲፭ ᵐ ፫ ኔፊ ፭፡፪።
፲፯ ᵐ ቅ.መ.መ. ሀይል።
፲፰ ᵐ ፪ ኔፊ ፴፫፡፭፣ አልማ ፪፡፲፱።
፲፱ ᵐ ቅ.መ.መ. መንፈስ—ክፉ መንፈሶች።
፳ ᵐ ፫ ኔፊ ፳፡፭።

በእውነት ገልጸዋል፤ እናም ደግሞ ምል ክቶችን አሳዩና፣ በህዝቡ መካከል ጥቂት ታምራቶችን ሰሩ።

፳፫ እንደዚህም ሠላሳ ሁለተኛውም ዓመት አለፈ። እናም በሠላሳ ሦስተኛው ዓመት መጀመሪያ ኔፊ ወደ ህዝቡ ጮኸ፤ እናም ንሰሃንና የኃጢያት ስርየትን ሰበከ ላቸው።

፳፬ እንግዲህ ወደ ንሰሃ ከመጡት በውሃ ᵐያልተጠመቀ አንድም እንደሌለ እንድታ ስታውሱ እፈልጋለሁ።

፳፭ ስለዚህ ንስሀ እንደገቡ እና ᵐለኃጥያ ታቸው ስርየት እንዳገኙ በእግዚአብሔር እና በህዝብ ፊት ምስክር እንዲሆን ወደእ ነርሱ የሚመጡትን እንደዚህ አይነት ሰዎ ችም በእነርሱ በውሀ እንዲጠመቁ ዘንድ፣ ለዚህም አገልግሎት ሰዎች በኔፊ ተሹመው ነበር።

፳፮ እናም በዚህ ዓመት መጀመሪያ ለን ስሃ የተጠመቁ ብዙዎች ነበሩ፤ እናም የዓ መቱ አብዛኛው ክፍል አለፈ።

ምዕራፍ ፳

ኃይለኛ ነፋስ፤ የመሬት መንቀጥቀጥ፤ እሳት፤ አውሎ ነፋስ እናም ታላቁ ጥፋት የክርስቶስን ስቅለት መሰከሩ—ብዙ ሰዎች ጠፉ—ምድርን ለሦስት ቀናት ጨለማ ሸፈናት—በህይወት የተረፉት ሰዎች በዕድላቸው አማረሩ። ፴፫–፴፬ ዓ.ም. ገደማ።

፩ እንግዲህ እንዲህ ሆነ በምዝገባችን መሰ ረት፣ እናም ምዝገባችን እውነት መሆኑን እናውቃለን፣ ምክንያቱም እነሆ፣ መዛግብ ቱን የጠበቀው ፃድቅ ሰው ነበርና—እርሱም ᵐበኢየሱስ ስም ብዙ ᶮታምራቶችን በእው ነት አድርጓል፤ እናም ሁለንተናውን ከክ ፋት ካላነፃው በስተቀር በኢየሱስ ስም ተአ ምራት ሊሰራ የሚቻለው ማንም ሰው አል ነበረም—

፪ እናም እንግዲህ እንዲህ ሆነ፣ በዚህ ሰው የጊዜአችን አቆጣጠር የተሳሳተ ካልሆነ፣ ᵐሠላሳ ሦስተኛው ዓመት አልፏል፤

፫ እናም ህዝቡ በላማናዊው ነቢዩ ሳሙ ኤል የተሰጠውን ምልክት፣ አዎን፣ በዚያ ጊዜም በምድሪቱ ገጽ ለሦስት ቀናት ᵐጨለማ ለሚሆንበት በታላቅ አትኩሮት መመልከት ጀመሩ።

፬ እናም ብዙ ᵐምልክቶች የተሰጡም ቢሆን፣ በህዝቡ መካከል ታላቅ መጠራ ጠር፣ እናም ፀብ መሆን ጀምሮ ነበር።

፭ እናም እንዲህ ሆነ በሠላሳ አራተኛው ዓመት በመጀመሪያው ወር፣ በወሩ በአ ራተኛው ቀን፣ በምድሪቱ ሁሉ በጭራሽ ታይቶ የማይታወቅ ታላቅ ውሽንፍር ተነሳ።

፮ እናም ደግሞ ታላቅና አስፈሪ የሆነ ኃይ ለኛ ነፋስም ነበር፤ እናም ምድሪቱን በሙሉ ᵐሲያንቀጠቅጥ የምትከፈት እስከሚመስል የሚያስፈራ ᶮነጎድጓድ ነበር።

፯ እናም በምድሪቱ ከዚህ በፊት የማይ ታወቅ እጅግ ኃይለኛ የሆነ መብረቅ ነበር።

፰ እናም ᵐየዛራሄምላ ከተማ ተቃጠለች።

፱ እናም የሞሮኒ ከተማ በባህሩ ውስጥ ሰጠመች፣ እናም በዚያ የሚኖሩ ሰዎች ሰጠሙ።

፲ እናም የሞሮኒህ ከተማም በአፈር ተሸ ፈነች፣ ስለዚህ በከተማዋም ፈንታ ታላቅ ተራራ ሆነ።

፲፩ እናም በምድሪቱ በስተደቡብ በኩል ታላቅና የሚያስፈራ ጥፋት ነበር።

፲፪ ነገር ግን እነሆ፣ በምድሪቱ በስተሰሜን በኩል ይበልጥ ታላቅና አስፈሪ የሆነ ጥፋት ነበር፤ እነሆም፣ በኃይለኛው ነፋስና፣ በአ ውሎ ነፋሱ፣ እናም በነጎድጓዱና መብረቁ፣

፳፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣ መጥመቅ።
፳፭ *ሀ* ት.እና ቃ. ፳፡ ፴፯።
ቅ.መ.መ. የኃጢያት ስርየት።
፳ ፩ *ሀ* የሐዋ. ፫፡ ፮፣ ያዕቆ. ፩፡ ፮።
ለ ፫ ኔፊ ፯፡ ፲፱–፳፣ ሞር. ፱፡ ፲፳–፲፱።
፪ *ሀ* ፫ ኔፊ ፪፡ ፳።
፫ *ሀ* ፩ ኔፊ ፲፱፡ ፲፣ ሔለ. ፲፩፡ ፳፡ ፳፯፣ ፫ ኔፊ ፲፡ ፱።
፬ *ሀ* ቅ.መ.መ. መስቀል።
፮ *ሀ* ማቴ. ፳፯፡ ፴፫፣ ፣ ፣–፣፩።
ለ ፩ ኔፊ ፲፱፡ ፲፩፣ ሔለ. ፲፩፡ ፳፩።
፳ *ሀ* ፬ ኔፊ ፩፡ ፮–፳።

እንዲሁም በምድሪቱም እጅግ ታላቅ በሆ
ነው መንቀጥቀጥ የምድሪቱ ገፅታ በሙሉ
ተለውጦ ነበር፤

፲፫ እናም ᵐአውራ ጎዳናዎች ተሰነጣጥ
ቀው ነበር፣ እናም የተስተካከለው መንገ
ድም ተበላሽቶ ነበር፤ ለጥ ያሉ ብዙ ስፍ
ራዎች ጎርባጣ ሆኑ።

፲፬ እናም ብዙ ታላላቅና ታዋቂ ከተ
ሞች ᵐሰጠሙ፣ እናም ብዙዎችም ተቃ
ጠሉና በከተሞቹ ያሉት ህንፃዎች በመሬት
ላይ እስከሚወድቁ ድረስ ተንቀጠቀጡና፣
በዚያ የነበሩት ነዋሪዎችም ተገደሉ እናም
ስፍራው ባዶ ሆነ።

፲፭ እናም ጥቂት ከተሞችም ተርፈው
ነበር፤ ነገር ግን የነበረው ጉዳት እጅግ ታላቅ
ነበር፤ እናም በእነርሱም ውስጥ ብዙ የተ
ገደሉ ነበሩ።

፲፮ እናም በአውሎ ነፋሱ የተወሰዱም
ጥቂቶች ነበሩ፤ እናም ከመወሰዳቸው በቀር
ወዴት እንደሄዱ የሚያውቅ ማንም አልነ
በረም።

፲፯ እናም ኃያሉ ነፋስ፤ እናም ነጎድጓ
ድና፣ መብረቅና፣ በመሬት መንቀጥቀጡ
የተነሳ ምድሪቱ ሙሉ በሙሉ ገፅታዋ ተለ
ወጠ።

፲፰ እናም እነሆ፣ ᵐአለቶቹም ተሰነጣ
ጠቁ፤ በምድረ ገፅ ላይም ሁሉ ተሰባበሩ፤
በዚህም የተነሳ በምድሪቱ ገፅ ላይ ሁሉ
የተቆራረጡ ብጥስጣሽና በቀጭኑ የተሰነ
ጣጠቁ፣ እናም ፍርክስካሽ ሆነው ተገኙ።

፲፱ እናም እንዲህ ሆነ ነጎድጓዱም፣ መብ
ረቁም፣ ውሽንፍሩም፣ ኃያሉ ነፋስ፣ እናም
የመሬት መንቀጥቀጡ በቆመበት ጊዜ—
እነሆም የቆየውም ለሦስት ሰዓታት ነበር፤
ጥቂት ሰዎችም ከዚህ በበለጠ ቆይቷል
ብለው ተናግረዋል፤ ይሁን እንጂ፣ እነዚህ
ታላቅና አስፈሪ ነገሮች ሁሉ የተከናወኑት
ᵐለሦስት ሰዓታት ነበር—እናም ከዚያ በኋላ
እነሆ፣ በምድሪቱ ገፅ ላይ ጨለማ ነበር።

፳ እናም እንዲህ ሆነ በምድሪቱ ገጽ ሁሉ
ላይም ጥቅጥቅ ያለ ጨለማ ነበር፤ በዚህም
የተነሳ ያልሞቱት በዚያን ስፍራ የነበሩትም
ነዋሪዎች ᵐየጨለማው ጭጋግ ᵃሊሰማቸው
ይችሉ ነበር፤

፳፩ እናም በጨለማውም የተነሳ ምንም
ብርሃን ሊሆን አልቻለም ነበር፤ ሻማም ሆነ
ችቦም በማንም ሰው ሊቀጣጠል አልቻለም፤
በምርጡ እናም እጅግ ደረቅ በሆነው እንጨ
ትም እሳት ሊቀጣጠል አልቻለም፤ ስለዚህ
ባጠቃላይ ምንም ብርሃን ሊሆን አልቻለም፤

፳፪ እናም በምድሪቱ ገፅ ላይ የነበረው
የጨለማ ጭጋግ እጅግ ታላቅ በመሆኑ እሳ
ትም ሆነ ጭላንጭል፤ ፀሐይም ሆነ ጨረቃ
እንዲሁም ከዋክብት አይታዩም ነበር።

፳፫ እናም እንዲህ ሆነ ᵐለሦስት ቀናትም
ምንም አይነት ብርሃን አልታየም ነበር፤
እናም በህዝቡ ሁሉ መካከልም የማያቋ
ርጥ ሀዘንና፣ ጩኸት፣ እንዲሁም ለቅሶ
ነበር፤ አዎን በጨለማውና በላያቸው ላይ
በመጣው ታላቅ ጥፋት የተነሳ የህዝቡ ለቅሶ
ታላቅ ነበር።

፳፬ እናም በአንድ ስፍራም እንዲህ በማ
ለት ሲጮኹ ተሰምተዋል፥ ከዚህ ታላ
ቅና አስፈሪ ከሆነው ቀን በፊት ንሰሃ ብን
ገባ ኖሮ፤ እናም ወንድሞቻችን ይተርፉና
በታላቁ ᵐየዛራሄምላም ከተማም በእሳቱ
ባልተቃጠሉም ነበር።

፳፭ እናም በሌላ ስፍራ እንዲህም በማለት
ሲጮኹና፣ ሲያዝኑ ተሰምተዋል፥ ከዚህ
ታላቅና አስፈሪ ከሆነው ቀን በፊት ንሰሃ
ብንገባ፣ እናም ነቢያትን ባንገድል፣ እን
ዲሁም በድንጋይ ባንወግራቸው፣ እንዲ
ሁም ባንወረውራቸው ኖሮ፤ ስለዚህ እና
ቶቻችንና፣ መልካም የሆኑት ሴቶች ልጆ
ቻችንና ልጆቻችን ይተርፉ ነበር፤ እናም
በታላቁ የሞሮኒሀ ከተማ አይቀበሩም ነበር።
እናም የህዝቡም ጩኸት እንደዚህ ታላቅና
አስፈሪ ነበር።

፲፫ ᵐ ሔለ. ፲፬፡፳፬፤
፫ ኔፊ ፮፡፳።
፲፬ ᵐ ፩ ኔፊ ፲፪፡፬።

፲፭ ᵐ ሔለ. ፲፬፡፳፩–፳፪።
፲፱ ᵐ ሉቃ. ፳፫፡፵፬።
፳ ᵐ ፩ ኔፊ ፲፪፡፭፤ ፲፱፡፲፩።

ᵃ ዘፀአ. ፲፡፳፩–፳፪።
፳፫ ᵐ ፩ ኔፊ ፲፱፡፲።
፳፬ ᵐ ሔለ. ፲፫፡፲፪።

ምዕራፍ ፱

በጭለማው ውስጥ፣ የክርስቶስ ድምጽ በክፋታቸው የተነሳ የብዙ ሰዎችን እንዲሁም የከተሞቹን ጥፋት አወጀ—መለኮታዊነቱንም ደግሞ አወጀ፣ የሙሴ ህግም እንደተሟላም አስታወቀ፣ እናም ሰዎችም ወደ እርሱ እንዲመጡ፣ እና እንዲድኑ ጋበዛቸው። ፴፬ ዓ.ም. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ በምድሪቱ ገጽ ሁሉ ላይ ባሉ ነዋሪዎቹ መካከል አንድ [ሀ]ድምፅ መጥቶ እንዲህ ሲል መጮኹ ተሰማ፥

፪ ለዚህ ህዝብ [ለ]ወዮ፣ ወዮ ወዮለት፣ ንሰሃ ካልገቡ በስተቀርም ለምድር ነዋሪዎች በሙሉ ወዮላቸው፤ መልካም የሆኑት የህዝቦቼ ወንዶችና ሴቶች ልጆች በመገደላቸው ዲያብሎስ [ሐ]ይስቃል፣ እናም መላ ዕክቶቹም ይደሰታሉና፤ እናም በክፋታቸውና በእርኩሰታቸው የተነሳ ነው የወደቁት!

፫ እነሆ፣ ታላቋን የዛራሄምላን ከተማ እናም ነዋሪዎችዋን በእሳት አቃጥያቸዋለሁ።

፬ እናም እነሆ፣ ታላቋን የሞሮኒን ከተማና በዚያም የሚገኙትን ነዋሪዎች በባህሩ ጥልቅ እንዲሰጥሙም አድርጌአለሁ።

፭ እናም እነሆ፣ ክፋታቸውንና ርኩሰታቸውን ከፊቴ ለመሸሸግ፣ የነቢያቱ እናም የቅዱሳን ደም ከእንግዲህ በኔ ላይ እንዳይመጣ ታላቋን የሞሮኒሀን ከተማና ነዋሪዎችዋን በመሬት ውስጥ ሸፍኜአቸዋለሁ።

፮ እናም እነሆ፣ የጌልገላ ከተማ እንድትሰጥም እናም በዚያን ስፍራ የሚገኙት ነዋሪዎችም በምድሪቱ ውስጥ እንዲቀበሩ አድርጌአለሁ፤

፯ አዎን፤ እናም የኦኒሀ ከተማና ነዋሪዎችዋ፤ እናም የሞኩም ከተማና ነዋሪዎችዋ፤ እናም የኢየሩሳሌም ከተማና ነዋሪዎችዋ፤ ከእንግዲህ ወዲያ የነቢያቱና የቅዱሳን ደም በእነርሱ ላይ ወደ እኔ እንዳይመጣ ክፋታቸውን እናም ርኩሰታቸውን ከፊቴ ለመሸሸግ በስፍራቸው [ሀ]ውሃ እንዲመጣባቸው አደረግሁ።

፰ እናም እነሆ፣ የጋድያንዲን ከተማና፣ የጋድዮምናን ከተማ፣ እናም የያዕቆብን ከተማና፣ የጊምጊምኖን ከተማ፣ በሙሉ እንዲሰምጡ አደረኳቸው፣ እናም በስፍራው [ለ]ኮረብታዎችንና ሸለቆዎችን ሰራሁ፤ ከእንግዲህም ወዲያ የነቢያቱና፣ የቅዱሳን ደም በእነርሱም ላይ ወደ እኔ እንዳይመጣ ክፋታቸውን፣ እናም ርኩሰታቸውን ከፊቴ ለመሸሸግ በስፍራው የነበሩትን ነዋሪዎች በመሬት ውስጥ ቀበርኳቸው።

፱ እናም እነሆ፣ ከምድር ኃጢአቶች ሁሉ በላይ በነበረው ኃጢአቶቻቸውና ክፋቶች፤ [ሀ]በሚስጥራዊው ግድያቸው፣ እንዲሁም በህብረታቸው የተነሳ ታላቋ ከተማ የንጉስ ያዕቆብ ህዝብ የሰፈረባት ያዕቆቡጋትን በእሳት እንድትቃጠል አደረግሁ፤ ምክንያቱም እነርሱ ነበሩ የህዝቤን ሠላም እናም የምድሪቱን አገዛዝ ያጠፉት፤ ስለዚህ ከእንግዲህም ወዲያ የነቢያቱምና የቅዱሳን ደም በእነርሱም ላይ ወደ እኔ እንዳይመጣ ከፊቴም [ሀ]ለማጥፋት እንዲቃጠሉ አደረግሁ።

፲ እናም እነሆ፣ ስለ ኃጢአታቸውና ርኩሰታቸው እንዲናገሩ የላኳቸውን ነቢያት በማስወጣት በሰሩት ክፋትና፣ በድንጋይ ስለወገሩአቸው፣ የላማን ከተማና፣ የኢዮሽ ከተማ፣ እናም የጋድ ከተማና፣ የቂሽቁመን ከተማ፣ እንዲሁም ነዋሪዎቻቸው በእሳት እንዲቃጠሉ አደረግሁ፤

፲፩ እናም ሁሉንም አስወጥተው ስለወረ ወሩአቸው፣ በመካከላቸውም ምንም ፃድቅ የሆነ ባለመኖሩ በመካከላቸውም የላኳቸው ነቢያትና፣ ፃድቃኖች ደም [ሀ]ከመሬት ወደ እኔ እንዳይጮህ ክፋቶቻቸው፣ እናም ርኩሰታቸው ከፊቴም ይደበቁ ዘንድ [ለ]እሳት ላኩባቸውና፣ አጠፋቸው።

፱ ፩ *ሀ* ፩ ኔፊ ፲፱፡ ፲፩፣ ፲፩፣ ፫ ኔፊ ፲፩፡ ፲፣ ፪ *ሀ* ማቴ. ፲፩፡ ፳–፳፩። *ለ* ሙሴ ፯፡ ፳፯።

፯ *ሀ* ሕዝ. ፳፯፡ ፲፱። ፰ *ሀ* ፩ ኔፊ ፲፱፡ ፲፩። ፱ *ሀ* ሌለ. ፮፡ ፲፯–፲፰፣ ፳፩። *ለ* ሞዛያ ፲፪፡ ፳።

፲፩ *ሀ* ዘፍጥ. ፱፡ ፲። *ለ* ፪ ነገሥ. ፩፡ ፱–፲፯፣ ሌለ. ፲፫፡ ፲፫።

፲፪ እናም በክፋቶቻቸውና በርኩሰታቸው የተነሳም በዚህች ምድር፣ እናም በዚህ ህዝብ ላይ [ሀ]ብዙ ታላቅ ጥፋቶች እንዲሆኑ አደረግሁ።

፲፫ አቤቱ ከእነርሱ የበለጠ ፃድቅ በመሆናችሁ እናንተ [ሀ]የተረፋችሁትን ሁሉ [ለ]እፈውሳችሁ ዘንድ ለኃጥያታችሁ ንስሃ ገብታችሁ እናም ተለውጣችሁ አሁን ወደ እኔ አትመለሱምን?

፲፬ አዎን በእውነት እላችኋለሁ፣ ወደ እኔ [ሀ]ከመጣችሁ [ለ]ዘለዓለማዊ ህይወትን ታገኛላችሁ። እነሆ የምህረት [ሐ]ክንዴ ወደ እናንተ ተዘርግታለች፣ እናም ማንም ቢመጣ እቀበለዋለሁ፣ እናም ወደ እኔ የሚመጡ የተባረኩ ናቸው።

፲፭ እነሆ እኔ የእግዚአብሔር ልጅ የሆንኩኝ ኢየሱስ ክርስቶስ ነኝ። ሰማያትንና ምድርን፣ እናም በውስጧ ያሉትን ነገሮች በሙሉ [ሀ]ፈጥሬአለሁ። ከመጀመሪያው ጀምሮ ከአብ ጋር ነበርኩኝ። [ለ]እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ አለ፤ በእኔም የአብ ስሙን አስከብሯል።

፲፮ የእኔ ወደሆኑት መጣሁና፣ የራሴ የሆኑትም [ሀ]አልተቀበሉኝም። እናም የእኔን መምጣት በተመለከተ ቅዱሳን መጻሕፍት ተፈጽመዋል።

፲፯ እናም ለተቀበሉኝ ሁሉ ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን [ሀ]ሰጠኋቸው፣ እናም በስሜ ለሚያምኑትም ሁሉ እንዲህም አደርጋለሁ፣ እነሆም በእኔም [ለ]ቤዛነት ይመጣልና በእኔም የሙሴ [ሐ]ህግ ተፈፅሟል።

፲፰ እኔ የአለም [ሀ]ብርሃንና ህይወት ነኝ። [ለ]አልፋና ኦሜጋ፤ የመጀመሪያ እና የመጨረሻ ነኝ።

፲፱ እናም ከእንግዲህ ደምን በማፍሰስ [ሀ]አታበረክቱልኝም፤ አዎን፣ መስዋእቶቻችሁና የሚቃጠሉት መስዋእቶች ማንኛውንም ስለማልቀበል መስዋእቶቻችሁ እናም የሚቃጠሉት መስዋእቶቻችሁ ይቆማሉ።

፳ እናም ለእኔም [ሀ]መስዋእት የተሰበረ ልብና የተዋረደ መንፈስ ታቀርባላችሁ። እናም ወደ እኔም በተሰበረ ልብና በተዋረደ መንፈስ የሚመጣ በእሳትና በመንፈስ ቅዱስ [ለ]አጠምቀዋለሁ፤ ላማናውያንን እንኳን ቢሆን በመለወጣቸው ወቅት በእኔ በነበራቸው እምነት የተነሳ በእሳት እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስ እንደተጠመቁት፣ እናም ይህንንም አያውቁም ነበር።

፳፩ እነሆ ዓለምን ከኃጢያት ለማዳን ለዓለም ቤዛነትን ለማምጣት ወደ ዓለም መጥቻለሁ።

፳፪ ስለዚህ [ሀ]ንስሃ የሚገባን እናም እንደህፃን [ለ]ልጅ ወደ እኔ የሚመጣንም እቀበለዋለሁ፣ የእግዚአብሔር መንግስትም እንደነዚህ ላሉት ናትና። እነሆ፣ እንደነዚህ ላሉትም ህይወቴን [ሐ]ሰጥቻለሁና፣ እናም በድጋሚም አንስቼዋለሁ፤ ስለዚህ የምድር ዳርቻ ሁሉ ንስሃ ግቡ፣ ወደ እኔም ኑና፣ ዳኑ።

ምዕራፍ ፲

በምድሪቱም ላይ ለብዙ ሰዓታት ዝምታ

፲፪ ሀ ፫ ኔፊ ፰፥፰–፲፣ ፲፬።
፲፫ ሀ ፫ ኔፊ ፲፥፲፪።
ለ ኤር. ፫፥፳፪፤
፫ ኔፊ ፲፰፥፴፪።
፲፬ ሀ ፪ ኔፊ ፳፮፥፳፬–፳፰፤
አልማ ፭፥፴፫–፴፮።
ለ ዮሐ. ፫፥፲፮።
ሐ አልማ ፲፱፥፴፮።
፲፭ ሀ ዮሐ. ፩፥፩–፫፤ ቄላ. ፩፥፲፮፤
ሔለ. ፲፬፥፲፪፤
ኤተር ፬፥፯፤
ት. እና ቃ. ፲፬፥፱።
ለ ዮሐ. ፲፯፥፳–፳፪፤
፫ ኔፊ ፲፩፥፳፯፤
፲፱፥፳፫፣ ፳፱።
፲፮ ሀ ዮሐ. ፩፥፲፩፤
ት. እና ቃ. ፮፥፳፩።
፲፯ ሀ ዮሐ. ፩፥፲፪።
ቅ.መ.መ. ሰው፣ ሰዎች—
የሰው እንደ እግዚአብሔር
አይነት ለመሆን ያለው
ችሎታ፤
የእግዚአብሔር ወንድ እና
ሴት ልጆች።
ለ ቅ.መ.መ. ቤዛ፣ ማዳን፣
ቤዛነት።
ሐ ፫ ኔፊ ፲፪፥፲፱፣ ፵፮–፵፯፤
፲፭፥፪–፱።
፲፰ ሀ ቅ.መ.መ. ብርሀን፣ የክርስቶስ
ብርሀን።
ለ ራዕ. ፩፥፰።
ቅ.መ.መ. አልፋ እና ኦሜጋ።
፲፱ ሀ አልማ ፴፬፥፲፫።
፳ ሀ ፫ ኔፊ ፲፪፥፲፱፤
ት. እና ቃ. ፳፥፴፯።
ለ ፪ ኔፊ ፴፩፥፲፫–፲፬።
፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣ ንስሀ
መግባት።
ለ ማር. ፲፥፲፭፤
ሞዛያ ፫፥፲፱፤
፫ ኔፊ ፲፩፥፴፯–፴፰።
ሐ ዮሐ. ፲፥፲፭–፲፰።

ሆነ—ዶሮ ጫጩቶችዋን እንደምትሰበ ስብ የክርስቶስ ድምፅም ህዝቡን ለመሰ ብሰብ ቃል ኪዳን ገባ—ፃድቃኖች የነበ ሩትም አብዛኞቹም ተጠብቀዋል። ፴፬–፴፮ ዓ.ም. ገደማ።

፩ እናም አሁን እነሆ፣ እንዲህ ሆነ በም ድሪቱ የነበሩት ሰዎች ሁሉ ይህንን ንግግር አድምጠዋል፣ እናም ስለዚያም መስክረ ዋል። እናም ከዚህ ንግግር በኋላ በምድሪቱ ላይ ለብዙ ሰዓታት ፀጥታ ነበር፤

፪ የህዝቡም መገረም ታላቅ በመሆኑ ስለ ተገደሉት ወገኖቻቸው ማልቀስ እናም መጮሃቸውን አቆሙ፣ ስለዚህ ለብዙ ሰዓ ታት በምድሪቱ ሁሉ ላይም ፀጥታ ነበር።

፫ እናም እንዲህ ሆነ ወደ ህዝቡም በድጋሚ ድምፅ እንዲህ ሲል መጣ፣ እናም ህዝቡ ሁሉ ሰምተውትና፣ መስክረውበት ነበር፥

፬ አቤቱ የእነዚህ የጠፉት [1]ታላላቅ ከተ ሞች ሰዎች፣ የያዕቆብ ዝርያዎች፣ አዎን፣ የእስራኤል ቤት የሆናችሁ፣ ዶሮ ጫጩት ዎችዋን በክንፎችዋ እንደምትሰበስብ ስንት ጊዜ ሰበሰብኳችሁ እናም [2]መገብኳችሁ።

፭ እናም በድጋሚ፣ ዶሮ ጫጩትዎችዋን በክንፎችዋ እንደምትሰበስብ ስንት ጊዜ ሰበ ሰብኳችሁ፣ አዎን፣ አቤቱ የእስራኤል ቤት የሆናችሁ የጠፋችሁት፤ አዎን፣ አቤቱ የእ ስራኤል ቤት የሆናችሁ እናንተ በኢየሩሳ ሌም የምትኖሩ፤ እናንት እንደ ጠፋችሁ ትም አይነት፤ አዎን፣ ዶሮ ጫጩትዎችዋን እንደምትሰበስብ ሁሉ እሰበስባችሁ ዘንድ [3]ስንት ጊዜ ወደድሁ፣ እናም እናንተ ግን አልወደዳችሁም።

፮ እናንተ [4]ያዳንኳችሁ የእስራኤል ቤት ሆይ፣ አቤቱ ንሰሃ ከገባችሁ እናም [5]በልባ ችሁ ሙሉ አላማ ወደ እኔ [6]ከተመለሳችሁ ዶሮ ጫጩትዎችዋን በክንፎችዋ ስር እን ደምትሰበስብ ስንት ጊዜ እሰበስባችኋለሁ።

፯ ካልሆነ ግን፣ የእስራኤል ቤት ሆይ፣ የአባቶቻችሁ [7]ቃል ኪዳን እስከሚፈፀም በት ጊዜ ድረስ የመኖሪያችሁ ስፍራ ባዶ ይሆናል።

፰ እናም አሁን እንዲህ ሆነ ህዝቡ እነዚ ህን ቃላት ከሰሙ በኋላ፣ እነሆ፣ ወገኖቻ ቸውንና ጓደኞቻቸውን በማጣታቸው በድ ጋሚ ማልቀስና መጮህ ጀመሩ።

፱ እናም እንዲህ ሆነ በዚህ ሁኔታ ሦስቱ ቀናት አለፉ። እናም በጠዋት ነበር፣ እናም [8]ጨለማው ከምድር ገጽ ላይም ተበተነ፣ ምድርም መንቀጥቀጥዋን አቆመች፣ አለ ቶችም መፈረካከሳቸውን አቆሙና፣ የሚ ያስፈራውም ማቃሰት ቆመ፤ እናም ሀይለኛ የነበረው ሁከትም ቆመ።

፲ እናም ምድሪቱ በአንድነት ተጣበቀ ችም፣ ጸናችም፤ እናም በህይወት የተ ረፉት ሰዎች ሀዘንና፣ ለቅሶ፣ እንዲሁም ዋይታም ቆመ፤ እናም ሀዘናቸው በደስታ፤ እንዲሁም ልቅሶአቸው ወደ ውዳሴና ወደ አዳኛቸው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም ምስ ጋና ተለወጠ፤

፲፩ እናም በነቢያቱ የተነገሩትም ቅዱሳን መፃህፍት እስከዚህ ድረስ [9]ተፈፅመዋል።

፲፪ እናም የዳኑትም [10]ይበልጥ ፃድቃን የነ በሩት ሰዎች ናቸውና፣ ነቢያትን የተቀበሉ ትና በድንጋይ ያልወገሩአቸውም እነርሱ ነበሩ፤ እናም የተረፉትም የቅዱሳንን ደም ያላፈሰሱት ነበሩ—

፲፫ እናም እነርሱም ድነዋልና፣ አል ሰመጡም፣ እንዲሁም በምድር ውስጥም አልተቀበሩም፤ በጥልቅ ባህሩ ውስጥም ሰጥመው አልቀሩም ነበር፤ እናም በእሳት አልተቃጠሉም፣ አልወደቁባቸውምና፣ በመደፋፈጥ አልሞቱም፤ እናም በአውሎ ነፋሱም አልተወሰዱም ነበር፤ በጭ ስና በጨለማውም ጭጋግ አልተሸነፉም ነበር።

---

[1] ፬ ሀ ፫ ኔፊ ፳፡ ፲፬።
ለ ፩ ኔፊ ፲፯፡ ፫።
[2] ሀ ማቴ. ፳፫፡ ፴፯፣
ት. እና ቃ. ፵፫፡ ፳፬–፳፭።
[3] ሀ ፫ ኔፊ ፱፡ ፲፫።
ለ ሕዝ. ፴፯፡ ፳፯።
ሐ ፩ ሳሙ. ፯፡ ፫፣
ሔለ. ፲፫፡ ፲፩፣
፫ ኔፊ ፳፬፡ ፯።
[4] ሀ ፫ ኔፊ ፳፡ ፲፱።
[5] ሀ የሐዋ. ፫፡ ፲፳–፳።
[6] ሀ ፪ ኔፊ ፳፯፡ ፳፣
፫ ኔፊ ፱፡ ፲፫።
[7] ሀ ፫ ኔፊ ፳፡ ፲፱።
[8] ሀ ፫ ኔፊ ፳፡ ፲፡ ሙሴ. ፯፡ ፲–፳።
[9] ሀ ፫ ኔፊ ፳፡ ፲፩።
[10] ሀ ፫ ኔፊ ፳፡ ፲፩።

፲፬ እናም አሁን ማንም የሚያነብ ይረዳ፤ ቅዱስ መጽሐፍ ያለው፣ [ሀ]ይመርምራቸው፣ እናም እነዚህ በእሳትና፣ በጭስ፣ እንዲሁም በኃይለኛው ነፋስ፣ እናም እነርሱን ለመዋጥ በመሬት [ለ]መከፈት የሆኑት ሞቶችና፣ ጥፋቶች ሁሉ፣ እናም እነዚህ ነገሮች ሁሉ የሆኑት የብዙዎቹ ቅዱሳን ነቢያት ትንቢቶች እንዲፈፀሙ እንደሆነም ይይና ይመልከት።

፲፭ እነሆ፣ እንዲህ እላችኋለሁ፣ አዎን፣ ብዙዎች በክርስቶስ መምጣት ስለእነዚህ ነገሮች መስክረዋል፣ እናም ስለእነዚህ ነገሮች በመመስከራቸው [ሀ]ተገድለዋል።

፲፮ አዎን፣ ነቢዩ [ሀ]ዜኖስ ስለነዚህ ነገሮች መሰከረ፣ እናም ደግሞ ዜኖቅ እነዚህን ነገሮች በተመለከተ ተናግሯል፣ ምክንያቱም እነርሱ በተለይ የዘሮቻቸው ቅሪት ስለሆነው ስለእኛ ተናግረዋል።

፲፯ እነሆ፣ አባታችን ያዕቆብ ደግሞ ስለ ዮሴፍ ዘር [ሀ]ቅሪቶች መስክሯል። እናም እነሆ፣ እኛ የዮሴፍ ዘር ቅሪቶች አይደለንምን? እናም ስለእኛ የሚመሰክሩት እነዚህ ነገሮች አባታችን ሌሂ ከኢየሩሳሌም ባመጣቸው የነሃስ ሰሌዳዎች ላይ አልተጻፉምን?

፲፰ እናም እንዲህ ሆነ በሠላሳ አራተኛው ዓመት መጨረሻ፤ እነሆ፣ የተረፉት የኔፊ ሰዎችና ደግሞ ላማናውያን ተብለው የሚጠሩት የተረፉት፣ ታላቅ ደግ ነገርን እንደተመለከቱ፣ እናም በራሳቸውም ላይ ታላቅ በረከት እንደፈሰሰባቸው አሳያችኋለሁ፤ በዚህም የተነሳ ክርስቶስ ወደ ሰማይ [ሀ]እንዳረገ ወዲያውም በእውነት ለእነርሱ እራሱን ገለፀላቸው—

፲፱ ሰውነቱን ለእነርሱ [ሀ]አሳያቸውና፣ አገለገላቸው፤ እናም የአገልግሎቱም ታሪክ ከዚህ በኋላ የሚሰጥ ይሆናል። ስለዚህ በዚህ ጊዜ ንግግሬን አቆማለሁ።

ህዝቡ በለጋስ ምድር በተሰበሰበበት ኢየሱስ ክርስቶስ ለኔፊ ህዝብ እራሱን ገለፀም፣ አስተማራቸውም፤ እናም በዚህ መንገድ ነበር እራሱን ያሳያቸው።

ምዕራፍ ፲፩ እስከ ፳፮ አጠቃሎ የያዘ።

ምዕራፍ ፲፩

አብ ስለተወደደው ልጁ መሰከረ—ክርስቶስ ተገለጠ፣ እናም ስለኃጢያት ክፍያው ተናገረ—ህዝቡም በእጁና በእግሩ፣ እናም በጎኑ ላይ የነበረውን የቁስሉን ምልክት ዳሰሱት—ሆሳዕና ብለውም ጮኹ—የጥምቀት ደንብና ስርዓት አስተማራቸው—የጸብ መንፈስ ከዲያብሎስ ነው—የክርስቶስ ትምህርት ሰዎች እንዲያምኑና፣ እንዲጠመቁ፣ እናም መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበሉ ነው። ፴፬ ዓ.ም. ገደማ።

፩ እናም አሁን እንዲህ ሆነ የኔፊ ህዝብ የሆኑ በቁጥር ብዙ የነበሩት በለጋስ ምድር በነበረው ቤተመቅደስ ዙሪያ በአንድነት ተሰብስበው ነበር፤ እናም እርስ በርሳቸውም ተገርመውና ተደንቀው ነበር፤ እናም አንዳቸው ለሌላኛቸውም [ሀ]ታላቅና አስገራሚ የነበሩትን ለውጦች እያሳዩ ነበር።

፪ እናም ደግሞ ስለሞቱ የተሰጠውን [ሀ]ምልክት ተሰጥቶ ስለነበረው ስለዚህ ስለኢየሱስ ክርስቶስ በተመለከተ ይነጋገሩ ነበር።

፫ እናም እንዲህ ሆነ እርስ በርሳቸው በሚነጋገሩበትም ወቅት፣ ከሰማይ የመጣ የሚመስል [ሀ]ድምፅ ሰሙ፤ የሰሙትንም ድምፅ ለመረዳት ባለመቻላቸው ዙሪያውን ተመለከቱ፤ እናም ድምፁ ሻካራ አልነበረም፣ ወይም የጩኸት ድምፅም አልነበረም፤ ይሁን እንጂ፣ [ለ]ድምፁ አነስተኛ ቢሆ

፲፬ ሀ ቅ.መ.መ. ቅዱሳት መጻህፍት—የቅዱሳት መጻህፍት ዋጋዎች።
ለ ፩ ኔፊ ፲፱፥፲፩፤ ፪ ኔፊ ፳፮፥፭።
፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. ሰማዕት፣ ሰማዕትነት።
፲፮ ሀ ሔለ. ፰፥፲፱–፳።
፲፯ ሀ ፪ ኔፊ ፫፥፬–፭፤ አልማ ፵፮፥፳፬፤ ፫ ኔፊ ፭፥፳፫–፳፬።
፲፰ ሀ የሐዋ. ፩፥፱–፲፩።
፲፱ ሀ ፫ ኔፊ ፲፩፥፲፪–፲፭።
፲፩ ፩ ሀ ፫ ኔፊ ፰፥፲፩–፲፬።
፪ ሀ ሔለ. ፲፬፥፳–፳፯።
፫ ሀ ዘዳግ. ፬፥፴፫–፴፮፤ ሔለ. ፭፥፳፱–፴፫።
ለ ፩ ነገሥ. ፲፱፥፲፩–፲፫፤ ት. እና ቃ. ፹፭፥፮።

ንም እንኳን የሰሙት ውስጣቸውን ሰንጥቆ ገብቶ፣ በዚህም የተነሳ ከሰውነታቸው ያል ተንቀሳቀሰ ክፍል አልነበረም፤ አዎን፣ እስ ከነፍሳቸው ድረስ ዘልቆ ገብቷል፣ እናም ልባቸውን እንዲቃጠል አድርጓል።

፩ እናም እንዲህ ሆነ በድጋሚ ድምፁን ሰሙት፣ እናም አልተረዱትም ነበር።

፪ እናም በድጋሚ ለሦስተኛ ጊዜ ድምፁን ሰሙትና፣ ለማዳመጥ ጆሮአቸውን ከፈቱ፤ እናም ዐይኖቻቸው ድምጹ ወደነበረበት እየተመለከቱ ነበር፤ ድምፁ ወደሚመጣ በት ወደ ሰማይ አቅጣጫም በፅናት ተመ ለከቱ።

፫ እናም እነሆ፣ ለሦስተኛ ጊዜም የሰሙ ትን ድምፅ ተረዱት፤ እንዲህም አላቸው፥

፬ እነሆ [ሀ]በእርሱ ደስ የሚለኝ፤ ስሜንም ያከበርኩበት፣ [ለ]የምወደው ልጄ ይህ ነው—እርሱን ስሙት።

፭ እናም እንዲህ ሆነ በተረዱትም ጊዜ በድጋሚ በሰማይ ላይ ዐይናቸውን ጣሉ፤ እናም እነሆ፣ አንድ ሰው ከሰማይ ሲወርድ [ሐ]ተመለከቱ፤ እናም እርሱ ነጭ ልብስ ለብሶ ነበር፤ እናም ወረደና በመካከላቸው ቆመ፤ እናም የህዝቡም ዐይን ሙሉ በሙሉ በእርሱ ላይ ነበር፣ እናም እርስ በርሳቸውም ለመነ ጋገር አልደፈሩም ነበር፣ እናም መላዕክት እንደታያቸው በማሰባቸውም ምን ማለት እንደሆነ አላወቁም ነበር።

፮ እናም እንዲህ ሆነ እርሱም እጁን ዘረ ጋና፣ ወደ ህዝቡም እንዲህ ሲል ተናገረ፥

፯ እነሆ፣ እኔ ኢየሱስ ክርስቶስ ነኝ፣ ነቢ ያት ወደ ዓለም ይመጣል ብለው የመሰከሩ ልኝም።

፲፩ እናም እነሆ እኔ የዓለም [ሀ]ብርሃንና ህይወት ነኝ፤ እናም አብ ከሰጠኝ መራራ [ለ]ፅዋም ጠጥቻለሁ፣ እናም የዓለምን ኃጢ ያት በራሴ ላይ [ሐ]በመውሰድም አብን አክብ ሬአለሁ፣ በዚህም ከመጀመሪያ ጀምሮ በሁ ሉም ነገሮች የአብን [መ]ፈቃድ ፈፅሜአለሁ።

፲፪ እናም እንዲህ ሆነ ኢየሱስም እነዚህን ቃላት በተናገረበት ጊዜ ሰዎቹ ሁሉ በመ ሬት ላይ ወደቁ፤ ምክንያቱም ክርስቶስ ወደ ሰማይ ካረገም በኋላ በመካከላቸው እራሱን እንደሚያሳይ በነቢያት [ሀ]ተተንብዮ እንደነ በር አስታውሰዋልና።

፲፫ እናም እንዲህ ሆነ ጌታም እንዲህ ሲል ተናገራቸው፥

፲፬ ተነሱ እናም እጆቻችሁንም በጎኔ [ሀ]እን ድታስገቡና ደግሞ የችንካሬን ምልክት በእ ጆቼና በእግሮቼ ላይ [ለ]ትዳስሱት ዘንድ፣ እኔ የእስራኤል [ሐ]አምላክ፣ እናም የምድር ሁሉ አምላክ መሆኔንና፣ [መ]ለዓለም ኃጥያቶችም መገደሌንም እንድታውቁ ዘንድ ወደ እኔ ኑ።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ ህዝቡም ሄዱና እጃ ቸውን በጎኑ አስገቡ፣ እናም ምስማር የተ ቸነከሩባቸውን እጆቹንና እግሮቹን ዳሰሷ ቸው፤ ሁሉም እስከሚደርሳቸው አንድ በአንድ እየሄዱ ይህን አደረጉ፣ እናም በዐይኖቻቸው ተመለከቱና፣ በእጆቻቸው ዳሰሱ፣ እናም በነቢያቱ ስለመምጣቱም የተነገረለት እርሱ [ሀ]መሆኑን በእርግጥም አወቁና መሰከሩ።

፲፮ እናም ሁሉም በሄዱና ለየራሳቸውም በተመለከቱ ጊዜ በአንድነት እንዲህ ሲሉ ጮኹ፥

፲፯ ሆሳዕና! የልዑሉ አምላካችን ስም የተባረከ ይሁን! እናም በኢየሱስ እግር ስር ወደቁ፣ እናም [ሀ]አመለኩት።

፲፰ እናም እንዲህ ሆነ እርሱም [ሀ]ለኔፊ

፲ ሀ ፲ ኔፊ ፱ ፡ ፲፭።
ለ ማቴ. ፲ ፡ ፲፮፣ ፲፯ ፡ ፭፣ ጆ.ስ.—ታ. ፭ ፡ ፲፯።
፡ ሀ ፭ ኔፊ ፲፪ ፡ ፮፣ ፪ ኔፊ ፳፯ ፡ ፭።
፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. ብርሀን፣ የክርስቶስ ብርሀን።
ለ ማቴ. ፳፯ ፡ ፴፱፣ ፶፪።
ሐ ዮሐ. ፭ ፡ ፳፱፣ ት. እና ቃ. ፲፱ ፡ ፲፰–፲፱።
መ ማር. ፲፬ ፡ ፴፮፣ ዮሐ. ፮ ፡ ፴፰፣ ት. እና ቃ. ፲፱ ፡ ፪።
፲፪ ሀ አልማ ፲፯ ፡ ፳።
፲፬ ሀ ዮሐ. ፳ ፡ ፳፯።
ለ ሉቃ. ፳፬ ፡ ፴፯–፴፱፣ ት. እና ቃ. ፲፳፱ ፡ ፪።
ሐ ኢሳ. ፶፫ ፡ ፫፣ ፲ ኔፊ ፲፭ ፡ ፭።
መ ፭ ኔፊ ፲፭ ፡ ፮።
፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—ክርስቶስ ከሚችነት በኋላ መገለጡ።
፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. ማምለክ።
፲፰ ሀ ፲ ኔፊ ፭ ፡ ፪፣ ፣ ።

ተናገረ (ኔፊ ከህዝቡ መካከል ስለነበር) እናም እርሱ ወደ ፊት እንዲመጣም አዘ ዘው።

፲፱ እናም ኔፊ ተነሳና፣ ሄደ እናም በጌታ ፊት አጎነበሰና፣ እግሮቹን ሳመ።

፳ እናም ጌታ እንዲነሳ አዘዘው። እናም እርሱም ተነሳና በፊቱ ቆመ።

፳፩ እናም ጌታ እንዲህ ሲል ተናገረው፥ በድጋሚ ወደ ሰማይ በማርግበት ጊዜም ይህንን ህዝብ ᵐእንድታጠምቅ ᵃስልጣንን እሰጥሃለሁ።

፳፪ እናም በድጋሚ ጌታ ᵐሌሎችን ጠርቶ በተመሳሳይ ተናገራቸው፤ እንዲያጠም ቁም ስልጣንን ሰጣቸው። እናም እንዲህ አላቸው፥ በዚህ መንገድ ታጠምቃላችሁ፤ በመካከላችሁም ᵃምንም ፀብ አይኖርም።

፳፫ በእውነት እንዲህ እላችኋለሁ በእ ናንተ ᵐቃላት አምኖ ለኃጢአቱ ንሰሃ የገ ባና በስሜም ለመጠመቅ ᵃየፈለጉትን በዚህ መንገድ አጥምቁአቸው—እነሆ፣ እናንተ ወርዳችሁ እናም በውሃው መካከል ᵃትቆማ ላችሁ፣ እናም በስሜም ታጠምቁአቸዋላ ችሁ።

፳፬ እናም አሁን እነሆ በስማቸውም ጠር ታችሁ የምትናገሩአቸው ቃላት እነዚህ ናቸው፥

፳፭ በኢየሱስ ክርስቶስ በተሰጠኝ ᵐስል ጣን መሰረት ᵃበአብ፤ በወልድ፤ እናም በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠምቅሃለሁ። አሜን።

፳፮ እናም በውሃ ውስጥ ᵐታጠልቋቸዋ ላችሁ፤ እናም ከውሃ ውስጥም በድጋሚ ታወጧቸዋላችሁ።

፳፯ እናም በዚህም መንገድ በስሜ ታጠ ምቃላችሁ፤ እነሆም፣ በእውነት አብና፣ ወልድ፣ እናም መንፈስ ቅዱስ ᵐአንድ ናቸው እላችኋለሁ፤ እናም እኔ በአብ እን ዳለሁ አብም በእኔ ነው፣ እናም አብና እኔም አንድ ነን።

፳፰ እናም በዚህ በማዛችሁ መሰረትም እንደዚህ አጥምቁ። እናም ከዚህ በፊት እንደነበረውም በመካከላችሁ ᵐፀብ አይኖ ርም፤ ከዚህ በፊት እንደነበረው በትምህ ርቴ ነጥቦችም ምክንያት በመካከላችሁ ፀብ አይኖርም።

፳፱ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ የፀብ ᵐመንፈስ ያለበት፣ የፀብ አባት ከሆነ እናም የሰዎችን ልብ እርስ በርስ ᵃእንዲጣሉ በቁጣ ከሚያነሳሳው ከዲያብሎስ እንጂ፤ ከእኔ አይደለም።

፴ እነሆ፣ ሰዎችን አንዳቸውን ከሌላኛው ልባቸውን ለቁጣ የሚያነሳሳ ይህ የእኔ ትም ህርት አይደለም፤ ነገር ግን እንደነዚህ ያሉ ነገሮች እንዲወገዱ ማድረግ ይህ የእኔ ትም ህርት ነው።

፴፩ እነሆ፣ እውነት፣ እውነት እላችኋ ለሁ፤ ᵐትምህርቴን ለእናንተ አውጃለሁ።

፴፪ እናም ይህ የእኔ ᵐትምህርት ነው፤ ይህም አብ ለእኔ የሰጠኝ ትምህርት ነው፤ ስለአብ ᵃእመሰክራለሁ፣ እንዲሁም አብ ስለእኔ ይመሰክራል፤ ᵃመንፈስ ቅዱስም ደግሞ ስለእኔና ስለአብ ይመሰክራል፤ በማ

፳፩ ᵐ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣ መጥመቅ።
ᵃ ቅ.መ.መ. ሀይል።
፳፪ ᵐ ፩ ኔፊ ፲፪፡ ፲፣ ፫ ኔፊ ፲፪፡ ፩።
ᵃ ፫ ኔፊ ፲፯፡ ፴፡ ፴፡ ፴ ኔፊ ፲፡ ፪።
፳፫ ᵐ ፫ ኔፊ ፲፪፡ ፪።
ᵃ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣ መጥመቅ—ለመጠመቅ ብቁነት።
ᵃᵃ ፫ ኔፊ ፲፱፡ ፲–፲፫።
፳፭ ᵐ ሞዛያ ፲፰፡ ፲፣ ፲፫፡ ት. እና ቃ. ፳፡ ፳፫።
ᵃ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣ መጥመቅ—ትክክለኛ ስልጣን።
ᵃᵃ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ።
፳፮ ᵐ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣ መጥመቅ—በማጥለቅ መጥመቅ።
፳፯ ᵐ ዮሐ. ፲፯፡ ፳–፳፪፣ ፫ ኔፊ ፳፰፡ ፲፡ ሞር. ፯፡ ፯፣ ት. እና ቃ. ፳፡ ፳፰።
፳፰ ᵐ ፩ ቆሮ. ፩፡ ፲፣ ኤፌ. ፬፡ ፲፩–፲፭፣ ት. እና ቃ. ፴፰፡ ፳፯።
፳፱ ᵐ ፪ ጢሞ. ፪፡ ፳፫–፳፬፣ ሞዛያ ፳፫፡ ፲፭። ቅ.መ.መ. ጸብ።
ᵃ ጆ.ስ.ት. ኤፌ. ፬፡ ፳፯ (ተጨማሪ)፣ ሞዛያ ፪፡ ፴፪–፴፫።
፴ ᵐ ፪ ኔፊ ፴፩፡ ፪–፳፩።
፴፩ ᵐ ቅ.መ.መ. የክርስቶስ ትምህርት።
ᵃ ፩ ዮሐ. ፭፡ ፯።
ᵃᵃ ፫ ኔፊ ፳፰፡ ፲፩፣ ኤተር ፭፡ ፬።

ንኛውም ስፍራ አብ ሰዎች በሙሉ ንሰሃ
እንዲገቡና በእኔ እንዲያምኑ አዞአቸዋል።
፴፤ እናም በእኔ ያመነና ᵐየተጠመቀ
ᵃይድናል፤ እና እነርሱም የእግዚአብሔ
ርን መንግስት ᵐየሚወርሱ ናቸው።
፴፪ እናም በእኔ የማያምን ቢኖርና ካልተ
ጠመቅ እርሱ ይኮነናል።
፴፫ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ይህ
የእኔ ትምህርት ነው፣ ከአብ መሆኑንም
እመሰክራለሁ፤ በእኔ ᵐየሚያምንም ቢኖር
ደግሞም በአብ ያምናል፤ ለእርሱም ስለ
እኔ አብ ይመሰክርለታል፤ አብም ᵃበእሳት
እንዲሁም ᵐበመንፈስ ቅዱስ ይጎበኘዋል።
፴፮ እናም አብ ስለእኔ ይመሰክራል፣
መንፈስ ቅዱስም ስለአብና ስለእኔ ይመ
ሰክራል፤ ምክንያቱም አብ እኔና መንፈስ
ቅዱስ አንድ ነን።
፴፯ እናም በድጋሚ እንዲህ እላችኋለሁ፣
ንሰሃ ግቡና እንደ ህፃናት ᵐሁኑ፤ በስሜም
ተጠመቁ፣ አለበለዚያ እነዚህን ነገሮች በም
ንም መንገድ ልትቀበሉ አትችሉም።
፴፰ እናም በድጋሚ እንዲህ እላችኋለሁ፣
ንሰሃ ግቡና በስሜም ተጠመቁ፣ እናም እን
ደህፃናት ሁኑ፣ አለበለዚያ በምንም መን
ገድ የእግዚአብሔርን መንግስት ልትወርሱ
አትችሉም።
፴፱ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣
ይህ የእኔ ትምህርት ነው፣ እናም በዚህም
ᵐየሚገነባ በእኔ አለት ላይ መሰረቱን የገነባ፣
እናም ᵃየሲዖል ደጆችም አያሸንፋቸውም።
፴ እናም ከዚህ የበለጠ ወይንም ያነሰ የሚ
ናገርና፣ ይህን እንደ ትምህርቴ የሚመሰርት
ቢኖር፣ እርሱ ከክፉ ነው፤ እናም በዓለት
ላይ የገነባ አይደለም፤ ነገር ግን ᵐበአሸዋው
ላይ መሰረቱን የገነባው ነው፣ የጥፋት ውሀ
ሲመጣና፣ ነፋስ ሲመታው የገሃነም ደጆ
ችም እርሱን ለመቀበል ክፍት ሆነው ይጠ
ብቃሉ።
፴፩ ስለዚህ ወደእነዚህ ህዝቦች ሂዱ፤ እስ
ከአለም ዳርቻም የተናገርኳቸውን ቃላት
አስተምሩአቸው።

ምዕራፍ ፲፪

*ኢየሱስ አስራ ሁለቱን ደቀመዛሙርት ጠራ
እናም ስልጣንን ሰጣቸው—በተራራው
ላይ እንዳደረገው ስብከት ለኔፋውያንም
አደረገ—ብፅዕናን ተናገራቸው—ትም
ህርቱም የላቀ ነበር እናም ከሙሴ ህግም
ቅድሚያ ያለው ነው—እርሱና አባቱ
ፍፁም እንደሆኑ እነርሱም ፍጹም እን
ዲሆኑ ታዘዋል—ማቴዎስ ፭ን አነጻፅሩ።
፴፪ ዓ. ም. ገደማ።*

፩ እናም እንዲህ ሆነ ኢየሱስ እነዚህን
ቃላት ለኔፋውያንና፣ ለተጠሩት በተናገ
ረበት ጊዜ፣ (የተጠሩት እናም ለማጥመቅ
ኃይልንና ስልጣንን የተቀበሉት ᵐአስራ
ሁለት ነበሩ) እናም እነሆ፣ እጁንም ወደ
ህዝቡ ዘረጋና እንዲህ ሲል ጮኸ፥ እናን
ተን እንዲያስተምሩና የእናንተ አገልጋዮች
እንዲሆኑ ከመካከላችሁ ᵃየመረጥኋቸውን
የእነዚህን የአስራ ሁለቱን ቃላት በጥንቃቄ
የምታዳምጡ ከሆነ ᵐየተባረካችሁ ናችሁ፤
እናም እነርሱ በውኃ ያጠምቋችሁ ዘንድ
ስልጣንን ሰጥቻቸዋለሁ፤ በውኃም ከተ
ጠመቃችሁ በኋላ፣ እነሆ፣ እኔ፣ በእሳትና
በመንፈስ ቅዱስ አጠምቃችኋለሁ፤ ስለ
ዚህ እኔን ከተመለከታችሁና፣ እኔ መሆኔን
ካወቃችሁ በኋላ በእኔ ካመናችሁና፣ ከተ
ጠመቃችሁ እናንተ የተባረካችሁ ናችሁ።
፪ እናም በድጋሚ፣ እናንተ እኔን ማየታ
ችሁንና እኔ መሆኔን ማወቃችሁን በመመ

፴፫ ሀ ማር. ፲፮፡ ፲፮።
ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣
መጥመቅ—አስፈላጊ።
ለ ቅ.መ.መ. ደህንነት።
ሐ ቅ.መ.መ. የሰለስቲያል
ክብር።
፴፭ ሀ ኤተር ፬፡ ፲፪።
ለ ፫ ኔፊ ፱፡ ፳፣ ፲፪፡ ፪።
ሐ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
፴፯ ሀ ማር. ፲፡ ፲፭፤
ሉቃ. ፲፰፡ ፲፯፤
ሞዛያ ፫፡ ፲፱፤
፫ ኔፊ ፱፡ ፳፪።
፴፱ ሀ ማቴ. ፯፡ ፳፭–፳፱፤
ሔለ. ፭፡ ፲፪።
ቅ.መ.መ. አለት።
ለ ፫ ኔፊ ፲፰፡ ፲፪–፲፫።
፴ ሀ ፫ ኔፊ ፲፡ ፳፡–፳፯።
፲፪ ፩ ሀ ፫ ኔፊ ፲፫፡ ፳፭።
ለ ቅ.መ.መ. ጥሪ፣
በእግዚአብሔር መጠራት፣
የተጠራበት።
ሐ ቅ.መ.መ. መባረክ፣
የተባረከ፣ በረከት።

ስከራችሁ በቃላችሁ ᵐያመኑት ይበልጥ የተ
ባረኩ ናቸው። አዎን፣ በቃላችሁ ያመኑት፣
እናም እራሳቸውን በጥልቅ ትህትና ᵃያወረ
ዱትና፣ የተጠመቁት የተባረኩ ናቸው፣
ᵇበእሳትና በመንፈስ ቅዱስ ይጎበኛሉ፣
እናም ለኃጢአታቸው ስርየትን ይቀበላሉና።

፲ አዎን፣ ᵐበመንፈስ ድሆች የሆኑ ወደ
እኔም ᵃየሚመጡ ብፁአን ናቸው፣ መን
ግስተ ሰማያት የእነርሱ ናትና።

፲፩ እናም ደግሞ የሚያዝኑ ብፁዐን ናቸው፣
መፅናናትን ያገኛሉና።

፲፪ እናም ᵐየዋሆች ብፁአን ናቸው፣ ᵃምድ
ርን ይወርሳሉና።

፲፫ እናም ᵐፅድቅን ᵃየሚራቡና ᵇየሚጠሙ
ሁሉ ብፁአን ናቸው፣ በመንፈስ ቅዱስ
ይሞላሉና።

፲፬ እናም ᵐምህረትን የሚያደርጉ ብፁአን
ናቸው፣ ምህረትን ያገኛሉና።

፲፭ እናም በልባቸው ᵐንፁሃን የሆኑ ሁሉ
ብፁአን ናቸው፣ እግዚአብሔርን ᵃያዩታ
ልና።

፲፮ እናም ᵐየሚያስተራርቁ ሁሉ ብፁአን
ናቸው፣ የእግዚአብሔር ᵃልጆች ይባላሉና።

፲፯ እናም ስለስሜ ᵐየሚሰደዱ ሁሉ ብፁአን
ናቸው፣ መንግስተ ሰማያት የእነርሱ ናትና።

፲፰ እናም ሰዎች ሲሰድቡአችሁና፣ ሲያ
ሳድዱአችሁና በሃሰትም ሁሉንም ዐይነት
ክፋት በእናንተ ላይ ስለእኔ ሲናገሩባችሁ፣
እናንተ ብፁአን ናችሁ፤

፲፱ ታላቅ ደስታም ይኖራችኋል እናም
እጅግ ትደሰታላችሁ፣ በሰማይም ᵐዋጋችሁ
ትልቅ ይሆናልና፤ ከእናንተም በፊት የነበሩ
ትን ነቢያት እንዲሁም አሳድደዋቸዋልና።

፲፫ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፥ እና
ንተ የምድር ᵐጨው እንድትሆኑ እሰጣችኋ
ለሁ፤ ነገር ግን ጨው ጣዕሙን ካጣ ምድር
እንዴት ትጣፈጣለች? ነገር ግን ለመጣል፣
እናም በሰዎች እግር በመረገጥ እንጂ
ጨውም ከዚያን ጊዜ በኋላ ከንቱ ይሆናል።

፲፬ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ የዚህ
ህዝብ ብርሃን እንድትሆኑ አሰጣችኋለሁ።
በኮረብታ ላይ ያለች ከተማ ልትሰወር አይ
ቻላትም።

፲፭ እነሆ፣ ሰዎች ᵐሻማ አብርተው ከዕን
ቅቡ በታች ያደርጉታልን? አይደለም፣
ነገር ግን በሻማ ማብሪያው ላይ ያደርጉ
ታል፣ እናም በቤቱ ውስጥ ላሉት ሁሉም
ብርሃንን ይሰጣል፤

፲፮ ስለዚህ እነዚህ ሰዎች መልካም ስራ
ዎቻችሁን ተመልክተው፣ እናም በሰማይ
ያለው አባታችሁን ያከብሩ ዘንድ ᵐብርሃ
ናችሁ በፊታቸው ሁሉ ይብራ።

፲፯ ህጉን ወይንም ነቢያትን ልሽር እን
ደመጣሁ አታስቡ። ለመሻር ሳይሆን የመ
ጣሁት ልፈፅመው ነው፤

፲፰ በእውነት እንዲህ እላችኋለሁ፣ ᵐከሕግ
አንዲት የወጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ
አታልፍም፣ ነገር ግን በእኔ ሁሉም ተፈፅ
ሟል።

፲፱ እናም እነሆ፣ በእኔ እንድታምኑ ዘን
ድና፣ ከኃጢአቶቻችሁ ንስሀ እንድትገቡ
ዘንድ፣ እናም ᵐበተሰበረ ልብ እና በተዋ
ረደ መንፈስ ወደ እኔ ትመጡ ዘንድ፣ የአባ
ቴን ህግና ትዕዛዛትን ሰጥቻችኋለሁ። እነሆ፣
ትዕዛዛቱ በፊታችሁ አሉ፣ እናም ᵃህጉም
ተፈፅሟል።

ᵇ ሀ ት. እና ቃ. ፴፯፡ ፲፫–፲፩።
ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
ለ ኤተር ፩፡ ፲፫–፲፭።
ሐ ፫ ኔፊ ፲፩፡ ፴፭፣ ፲፱፡ ፲፫።
ᶜ ሀ ት. እና ቃ. ፴፯፡ ፲፯–፲፰።
ቅ.መ.መ. ትሁት፣ ትሕትና።
ለ ማቴ. ፲፩፡ ፳፱–፴።
ᵈ ሀ ሮሜ ፲ᵇ፡ ፲፯፣
ሞዛያ ᶜ፡ ፲፱።
ቅ.መ.መ. ገር፣ ገርነት።
ለ ቅ.መ.መ. ምድር።

ᵉ ሀ ምሳ. ፳፩፡ ፳፩።
ለ ᵇ ኔፊ ፱፡ ፻፩፣
ኢኖስ ፩፡ ፱።
ሐ ኤር. ፳፱፡ ፲ᶜ።
ᶠ ሀ ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።
ᵍ ሀ ቅ.መ.መ. ንጹህ፣ ንጹህነት።
ለ ት. እና ቃ. ፻ᶜ፡ ፩።
ʰ ሀ ቅ.መ.መ. ሰላም የሚሰራ።
ለ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር
ወንድ እና ሴት ልጆች።
ᶦ ሀ ት. እና ቃ. ፻፳፪፡ ፭–፱።
ቅ.መ.መ. ማሳደድ፣
መሳደድ።
ᶠ ᵇ ሀ ኤተር ፲ᵇ፡ ፱።
ᶠᶠ ᵇ ሀ ት. እና ቃ. ፻፩፡ ፴፱–፴።
ቅ.መ.መ. ጨው።
ᶠᶠ ᶜ ሀ ሉቃ. ᵍ፡ ፲ᶠ።
ᶠᶠ ᵈ ሀ ᶠ ኔፊ ፲ᵍ፡ ᵍ፱።
ᶠᶠ ᵉ ሀ ቅ.መ.መ. የሙሴ ህግ።
ᶠᶠ ᶠ ሀ ᶠ ኔፊ ᶠ፡ ᵍ።
ቅ.መ.መ. የተሰበረ ልብ።
ለ ᶠ ኔፊ ᶠ፡ ᶠᶠ።

፳ ስለዚህ ወደ እኔ ኑ፣ እናም ዳኑ፤ እውነት
እላችኋለሁና፣ በዚህ ጊዜ ያዘዝኳችሁን ትዕ
ዛዛት ካልጠበቃችሁ በቀር፣ በምንም ምክ
ንያት ወደ መንግስተ ሰማያት አትገቡም።
፳፩ በጥንት ጊዜም በነበሩት አትግደሉ
ሲባል ሰምታችኋል፤ እናም ደግሞ በእና
ንተ ፊትም ተፅፎአል፣ እና ᵐየገደለም በእ
ግዚአብሔር ፍርድ አደጋ ላይ ይሆናል፤
፳፪ ነገር ግን እንዲህ እላችኋለሁ፣ በወን
ድሙ ላይ የሚቆጣ በእግዚአብሔር ቅጣት
አደጋ ላይ ይሆናል። እናም ወንድሙን
ጨርቃም ብሎ የሚናገር ቢኖር በምክሩ
አደጋ ላይ ነው፤ እናም ሞኝ ብሎ የሚናገ
ርም በገሃነሙ እሳት አደጋ ላይ ነው።
፳፫ ስለዚህ ወደእኔ ብትመጡ ወይንም
ለመምጣት የምትፈልጉ ከሆናችሁ፣ እናም
ወንድማችሁ በእናንተ ላይ አንድ ነገር እን
ዳለው ካስታወሳችሁ፤
፳፬ ወደ ወንድማችሁም ሂዱ፣ እናም
በመጀመሪያ ከወንድማችሁ ጋር ᵐተስ
ማሙ፤ እናም በልባችሁ ሙሉ ዓላማ ወደ
እኔ ኑ፣ እናም እኔ እቀበላችኋለሁ።
፳፭ ከጠላታችሁ ጋር በአንድ መንገድ
ስትሆኑ ፈጥናችሁ ተስማሙ፣ ያለበለዚያ
ብልጫ እንዳያገኝባችሁ፣ እናም ወደ ወህኒ
እንዳትጣሉ።
፳፮ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ያለ
ባችሁን ሰኒን እስከምትከፍሉ ከዚያ በም
ንም መንገድ አትወጡም። እናም በወህኒ
በሆናችሁ ጊዜ አንድ ᵐሰኒን እንኳን ለመ
ክፈል ትችላላችሁን? እውነት እላችኋለሁ
አትችሉም።
፳፯ እነሆ፣ ᵐአታመንዝር ተብሎ በጥን
ቶቹ ተጽፏል፤
፳፰ ነገር ግን እንዲህ እላችኋለሁ፣ ወደ
ሴት ያየ ሁሉ ᵐየተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ
ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል።
፳፱ እነሆ፣ እናንተ ከእነዚህ ነገሮች ማን
ኛውም ወደ ᵐልባችሁ እንዲገባ አትፍቀዱ
ትዕዛዛትን ሰጥቻችኋለሁ፤
፴ ወደገሃነም ከምትጣሉ ይልቅ በእነዚ
ህም ነገሮች ራሳችሁን ብትክዱ፣ ᵐመስ
ቀላችሁንም ብትሸከሙ የተሻለ ይሆናል።
፴፩ ሚስቱን የሚፈታ ህጋዊ ᵐየፍቺ ማስ
ረጃ ይስጣት የሚል ተፅፏል።
፴፪ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ᵐበማ
መንዘር ምክንያት ካልሆነ በቀር ሚስቱን
ᵃየሚፈታ ቢኖር፣ ᵇዝሙት እንድትፈጽም
ያደርጋታል ማለት ነው፤ እናም የተፈታች
ውን የሚያገባ ዝሙትን ፈፅሟል።
፴፫ እናም በድጋሚ በውሸት አትማል ነገር
ግን ᵐመሐላዎችህን ለጌታ ስጥ እንደተባለ
ሰምታችኋል፤
፴፬ ነገር ግን እውነት፣ እውነት እላችኋ
ለሁ፣ በፍፁም ᵐአትማሉ፤ የአምላክ ዙፋን
ነውና፣ በሰማይም ቢሆን አትማሉ፤
፴፭ ምድርም የእግሩ መረገጫ ናትና በእ
ርሷም አትማሉ፤
፴፮ በራሳችሁም አትማሉ፣ ምክንያቱም
ከራሳችሁ አንዲት ፀጉር እንኳን ጥቁር ወይ
ንም ነጭ ለማድረግ አትችሉምና፤
፴፯ ነገር ግን ቃላችሁ አዎን፣ አዎን፣
አይደለም፣ አይደለም ይሁን፤ ከዚህ የበ
ለጠ የተባለም ከክፉ ነውና።
፴፰ እናም እነሆ፣ ᵐለዐይን ዐይን፣ እንዲ
ሁም ለጥርስ ጥርስ ተብሎ ተፅፏል፤
፴፱ ነገር ግን እላችኋለሁ፣ ᵐከመጥፎ
ጋር አትታገሉ፣ ነገር ግን ቀኝ ጉንጭህን
በጥፊ ለሚመታህ ሁሉ ሁለተኛውን ደግሞ
ᵃአዙርለት፤

፳፩ ሀ ዘፀአ. ፳፡ ፲፫፣
ሞዛያ ፲፫፡ ፳፩፤
ት. እና ቃ. ፴፪፡ ፲፰።
፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. ይቅርታ
ማድረግ።
፳፮ ሀ አልማ ፲፩፡ ፫።
፳፯ ሀ ፪ ኔፊ ፱፡ ፴፯፣
ት. እና ቃ. ፶፱፡ ፯።
፳፰ ሀ ት. እና ቃ. ፴፪፡ ፳፫።
ቅ.መ.መ. ምኞት።
፳፱ ሀ የሐዋ. ፰፡ ፳፪።
፴ ሀ ማቴ. ፲፡ ፴፰፣
፲፯፡ ፳፬፣
ሉቃ. ፱፡ ፳፫።
፴፩ ሀ ቅ.መ.መ. መፋታት።
፴፪ ሀ ቅ.መ.መ. ዝሙት መፈጸም።
ለ ማር. ፲፡ ፲፩–፲፪።
ሐ ቅ.መ.መ. ማመንዘር።
፴፫ ሀ ቅ.መ.መ. መሀላ።
፴፬ ሀ ቅ.መ.መ. ማራከስ።
፴፰ ሀ ዘሌዋ. ፳፬፡ ፳።
፴፱ ሀ ፫ ኔፊ ፮፡ ፲፫፣
፬ ኔፊ ፩፡ ፴፬፣
ት. እና ቃ. ፶፰፡ ፳፫–፴፪።
ለ ቅ.መ.መ. ትዕግስት።

፵ እናም ማንኛውም ሰው በህግ ፊት ቢያ
ቀርባችሁ፣ እናም እጀጠባባችሁን ቢወስድ
መጎናፀፊያችሁን ደግሞ እንዲወስድ ፍቀ
ዱለት፤
፵፩ እናም ማንም ሰው አንድ ምዕራፍ
ትሄድ ዘንድ ቢያስገድድህ ሁለተኛውን
ከእርሱ ጋር ሂድ።
፵፪ ለሚጠይቅህ ᵐስጠው፣ እናም ከአንተ
ለመበደር የሚፈልግንም አትከልክለው።
፵፫ እናም እነሆ ደግሞ ባልንጀራህን ውደ
ድና ጠላቶችህን ጥላ ተብሎ ተፅፏል፤
፵፬ ነገር ግን እነሆ፣ ᵐጠላቶቻችሁን
ውደዱ፤ የሚረግሟችሁንም ባርኩ፤ ለሚ
ጠሏችሁም መልካምን አድርጉ፣ እናም
በከንቱ የሚነቅፉአችሁንና የሚያሳድዱአ
ችሁን ᵃጸልዩላቸው እላችኋለሁ።
፵፭ በሰማይ ያለው የአባታችሁ ልጆች
እንድትሆኑም፤ ፀሀዩንም ለመጥፎ እና
ለመልካም ሰዎች እንድትወጣ ያደርጋልና።
፵፮ ስለዚህ በጥንት ጊዜ በህጉ ስር የነበሩ
ትም እነዚያ ነገሮች፣ በእኔ ሁሉም ተፈፅ
መዋል።
፵፯ ᵐበጥንት የነበሩት ነገሮች ተፈፅመ
ዋል፣ እናም ሁሉም ነገሮች አዲስ ሆነዋል።
፵፰ ስለዚህ እንደእኔ ወይንም በሰማይ
እንዳለው ᵐፍፁም እንደሆነው አባታችሁ
ፍፁም እንድትሆኑ እፈልጋችኋለሁ።

ምዕራፍ ፲፫

*ኢየሱስ ለኔፋውያን የጌታን ፀሎት አስተ
ማረ—በሰማይ ሀብትን ማስቀመጥ ይገባ
ቸዋል—አስራ ሁለቱ ሐዋርያት በአገል
ግሎታቸው ወቅት ስለጊዜያዊ ነገሮች እን
ዳያስቡ ታዘዙ—ማቴዎስ ፮ን አነጻፅሩ።
ግ.ዘ. ፳፱ ዓ.ም. ገደማ።*

፩ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ ለድሆች
ᵐምፅዋት እንድትሰጡ እፈልጋለሁ፤ ነገር
ግን ለሰዎች ትታዩ ዘንድ ምጽዋታችሁን
በፊታቸው እንዳታደርጉ ተጠንቀቁ፤ አለ
በለዚያ በሰማይ ካለው አባታችሁ ዘንድ ዋጋ
አይኖራችሁም።
፪ ስለዚህ፣ ምፅዋታችሁን ስትሰጡ
ግብዞች በሰዎች ዘንድ ᵐክብር ይኖራቸው
ዘንድ በምኩራብ እናም በጎዳናዎች እንደ
ሚያደርጉት መለከት አታስነፉ። እውነት
እላችኋለሁ እነርሱ ዋጋቸውን አግኝተዋል።
፫ ነገር ግን መፅዋዕትን በምትሰጡበት ጊዜ
ቀኝ እጃችሁ ግራ እጃችሁ የሚያደርገውን
አይወቅ፤
፬ ምፅዋታችሁ በስውር እንዲሆን፤ እናም
በስውር የሚያያችሁ አባታችሁ በግልፅ
ይከፍላችኋል።
፭ እናም በምትፀልዩበት ጊዜ እንደግብዞች
አትሁኑ፤ ምክንያቱም እነርሱ በምኩራብ
እናም በየመንገዱ ዳርቻ በመቆም በሰዎች
ለመታየት ᵐመፀለይን ይወዳሉ። እውነት
እላችኋለሁ፥ ዋጋቸውን ተቀብለዋል።
፮ ነገር ግን በምትፀልዩበት ጊዜ ወደ
እልፍኛችሁ ውስጥ ግቡ፣ እናም በራችሁ
ንም በምትዘጉበት ጊዜ፣ በስውር ወዳለው
አባታችሁ ፀልዩ፣ እናም በስውር የሚያ
ያችሁ አባታችሁ በግልፅ ይከፍላችኋል።
፯ ነገር ግን አሕዛብም በመናገራቸው ብዛት
እንደሚሰሙ ይመስላቸዋልና፣ በምትፀል
ዩበት ጊዜ እንደ እነርሱ በከንቱ አትድገሙ።
፰ ስለዚህ እናንተ እንደ እነርሱ አትምሰሉ፣
ምክንያቱም አባታችሁን ከመጠየቃችሁ
በፊት ምን እንደምትፈልጉ ᵐያውቃልና።
፱ ስለዚህ እንዲህ ᵐብላችሁ ᵃፀልዩ፥ በሰ
ማይ የምትኖር ᵇአባታችን ሆይ፣ ስምህ
ይቀደስ።

፵፪ ሀ ያዕቆ. ፪፡፲፯–፲፱፤
ሞዛያ ፬፡ ፳፪–፳፯።
፵፬ ሀ ምሳ. ፳፬፡ ፲፯፣
አልማ ፵፰፡ ፳፫።
ለ የሐዋ. ፯፡ ፶፱–፷።
፵፯ ሀ ፲ ኔፊ ፲፯፡ ፪፣ ፯፣
ት.እና ቃ. ፳፪፡ ፩።
፵፰ ሀ ማቴ. ፭፡ ፵፰፤
፲ ኔፊ ፳፯፡ ፳፯።
ቅ.መ.መ. ፍጹም።
፲፫ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. ምፅዋት፣
የምፅዋት ስጦታ።
፪ ሀ ት.እና ቃ. ፲፳፩፡ ፵፬–፵፭።
፫ ሀ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
፬ ሀ ት.እና ቃ. ፹፬፡ ፹፫።
፭ ሀ ማቴ. ፮፡ ፭–፲፣
ለ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
ሐ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣
አምላክ—እግዚአብሔር
አብ።

፲ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም
በምድር ትሁን።
፲፩ እናም የበደሉንን ይቅር እንደምንል፣
በደላችንን ይቅር በለን፤
፲፪ ከክፉ አድነን እንጂ፣ እናም ወደ ፈተ
ናም ᵐአታግባን።
፲፫ መንግሥት ያንተ ናትና፣ እና ሀይ
ልም፣ ክብርም ለዘላለሙ አሜን።
፲፬ ለሰዎች በደላቸውን ይቅር የምትሉ
ከሆነ፣ የሰማዩ አባታችሁ ደግሞ ᵐይቅር
ይላችኋል፤
፲፭ ለሰዎች ግን ኃጢአታቸውን ይቅር
ባትሉ፥ አባታችሁም ኃጢአታችሁን ይቅር
አይላችሁም።
፲፮ ከዚህም በተጨማሪ፣ ᵐበምትጾሙ
በት ጊዜ ፊታቸውን እንደሚያጠወልጉት
እንደግብዞች አትሁኑ፤ ምክንያቱም ለሰ
ዎች እንደያመኛ ሊታዩ ፊታቸውን ያጠወ
ልጋሉና። እውነት እላችኋለሁ፣ ዋጋቸውን
ተቀብለዋል።
፲፯ ነገር ግን እናንተ በምትጾሙበት
ወቅት ራሳችሁን ተቀቡ፤ እናም ፊታች
ሁን ታጠቡ፤
፲፰ ᵐበስውር ላለው አባታችሁ እንጂ እንደ
ጦመኛ ለሰዎች እንዳትታይ፤ በስውር የሚ
ያያችሁ አባታችሁም በግልፅ ዋጋችሁን
ይከፍላችኋል።
፲፱ ብልና ዝገት በሚያጠፉት፣ ሌቦችም
ቆፍረው በሚሰርቁት፣ ለራሳችሁ በምድር
ላይ ሀብትን አታከማቹ፤
፳ ነገር ግን ብልና ዝገት የማያጠፋውን፣
እናም ሌቦች ቆፍረው የማይሰርቁትን፣ ለራ
ሳችሁ የሚሆን ᵐሀብትን በሰማይ አከማቹ።
፳፩ ሀብታችሁ ባለበት ልባችሁ ደግሞ
በዚያ ይሆናልና።
፳፪ የሰውነት ᵐብርሀን ዐይን ናት፤ ስለ
ዚህ ዐይናችሁ ቀና ብትሆን ሰውነታችሁ
ሁሉ ብሩህ ይሆናል።
፳፫ ነገር ግን ዐይናችሁ ክፉ ብትሆን ሰው
ነታችሁ ሁሉ የጨለመ ይሆናል። ስለዚህ
በእናንተ ያለው ብርሃን ጨለማ ቢሆን ጨለ
ማው እንዴት የበረታ ይሆናል!
፳፬ ማንም ሰው ለሁለት ጌቶች ᵐማገልገል
አይቻለውም፤ ምክንያቱም አንዱን ይጠላ
ልና ሌላኛውን ይወዳል፣ ወይም ወደ አንዱ
ይጠጋል፣ እናም ሌላኛውን ይንቃል። እግ
ዚአብሔርን ማገልገልና ለገንዘብ መገዛት
አትችሉም።
፳፭ እናም እንግዲህ እንዲህ ሆነ ኢየ
ሱስ እነዚህን ቃላት በሚናገርበት ወቅት
ወደ መረጣቸው አስራ ሁለቱ ተመለከተ፣
እናም እንዲህ አላቸው፥ የተናገርኳቸ
ውን ቃላት አስታውሱ። እነሆም፣ እና
ንተ ህዝብን ᵐእንድታገለግሉ የመረጥኳ
ችሁ ናችሁ። ስለዚህ ስለህይወታችሁ በም
ትበሉትም ሆነ በምትጠጡት ስለሰውነታ
ችሁ በምትለብሱትም ᵃአትጨነቁ። ህይ
ወት ከመብል እንዲሁም ሰውነት ከልብስ
አይበልጥምን?
፳፮ ወደ ሰማይ ወፎች ተመልከቱ፤ አይ
ዘሩም አያጭዱምም በጎተራም አይከቱም፤
ነገር ግን የሰማዩ አባታችሁም ይመግባቸ
ዋል፤ እናንተ ከእነርሱ የተሻላችሁ አይ
ደላችሁምን?
፳፯ ከእናንተ ተጨንቆ በቁመቱ ላይ አንድ
ክንድ መጨመር የሚችል ማነው?
፳፰ እናም ስለልብስ ለምን ትጨነቃላ
ችሁ? የሜዳ አበቦች እንዴት እንደሚያ
ድጉ ልብ ብላችሁ ተመልከቱ፤ አይደክ
ሙም፣ አይፈትሉም፤
፳፱ እናም ግን እንዲህ እላችኋለሁ፣
ሰለሞንስ እንኳ በክብሩ ሁሉ ከእነዚህ እን
ደአንዱ አልለበሰም።
፴ ስለዚህ፣ እግዚአብሔር ዛሬ ያለውን
ነገም ወደ እቶን የሚጣለውን የሜዳን ሳር
በዚህ ሁኔታ የሚያለብሰው ከሆነ፣ እናን

፲፪ ᵐ ጆ.ስ.ት. ማቴ. ፮፡ ፲፬ (ተጨማሪ)።
፲፬ ᵐ ሞዛያ ፳፮፡ ፴–፴፩፤ ት. እና ቃ. ፳፱፡ ፱። ቅ.መ.መ. ይቅርታ ማድረግ።
፲፮ ᵐ ኢሳ. ፶፰፡ ፭–፯። ቅ.መ.መ. ጾም፣ መጾም።
፲፰ ᵐ ት. እና ቃ. ፴፯፡ ፯።
፳ ᵐ ሉሌ. ፭፡ ፲፤ ፲፡ ፳፭።
፳፪ ᵐ ት. እና ቃ. ፹፯፡ ፳፯።
፳፭ ᵐ ᵃ ሳሙ. ፯፡ ፲።
፳፭ ᵐ ቅ.መ.መ. አገልግሎት። ᵃ አልማ ፴፭፡ ፴፯–፴፰፤ ት. እና ቃ. ፹፱፡ ፳፱–፹፭።

ተም እምነት የጎደላችሁ ካልሆናችሁ እን ዲሁ እናንተንም ያለብላችኋል።

፴፭ ስለዚህ ምን እንበላለን? ምን እንጠ ጣለን? ምንስ እንለብሳለን? ብላችሁ ምንም አታስቡ።

፴፮ የሰማይ አባታችሁ እነዚህን ነገሮች በሙሉ እንደምትፈልጉ ያውቃልና።

፴፯ ነገር ግን በመጀመሪያ የእግዚአብሔ ርን [ሀ]መንግስትና ፅድቁን ፈልጉ፣ እናም እነዚህ ነገሮች በሙሉ ይጨመሩላችኋል።

፴፰ ስለዚህ ነገ ለራሱ ነገሮች ይጨነቃ ልና ለነገ ምንም አትጨነቁ። ለክፋቱ ቀኑ ብቁ ነውና።

ምዕራፍ ፲፰

አትፍረዱ፤ እግዚአብሔርን ጠይቁ፤ ከሃ ሰተኛ ነቢያት ተጠንቀቁ በማለት ኢየሱስ አዘዘ—የአባታቸውን ፈቃድ ለሚያደርጉ የደህንነትን ቃል ገብቶላቸዋል—ማቴዎስ ፯ን አነጻፅሩ። ፴፱ ዓ.ም. ገደማ።

፩ እናም አሁን እንዲህ ሆነ ኢየሱስ እነዚ ህን ቃላት በተናገረ ጊዜ በድጋሚ ወደ ህዝቡ ተመለሰ፣ እናም በድጋሚ አፉን ከፍቶ እን ዲህ አላቸው፥ እውነት፣ እውነት እላችኋ ለሁ እንዳይፈረድባችሁ [ሁ]አትፍረዱ።

፪ [ሁ]በምትፈርዱበት ፍርድ ይፈረድባች ኋልና፤ እናም በምትሰፍሩበትም መስፈ ሪያ ደግሞም ይሰፈርላችኋል።

፫ እናም በወንድማችሁ ዐይን ያለውን ጉድፍ ስለምን ታያላችሁ፤ ነገር ግን በዐ ይናችሁ ያለውን ምሰሶ ስለምን አትመለ ከቱም?

፬ ወይም ወንድማችሁን ከዐይንህ ጉድፍ ላውጣ ፍቀድልኝ እንዴትስ ትሉታላችሁ? እናም እነሆ በዐይናችሁ ምሰሶ አለ።

፭ እናንተ ግብዞች አስቀድማችሁ በዐ ይናችሁ ያለውን [ሁ]ምሰሶ አውጡ፤ እናም ከዚያም በኋላ ከወንድማችሁ ዐይን ጉድ ፉን ታወጡ ዘንድ አጥርታችሁ ታያላችሁ።

፮ በእግራቸው እንዳይረግጡት ተመል ሰውም እንዳይነክሱአችሁ [ሁ]የተቀደሰውን ለውሾች አትስጡ፤ ዕንቁዎቻችሁንም በእ ሪያዎች ፊት አትጣሉ።

፯ [ሁ]ለምኑ፣ ይሰጣችኋል፤ ፈልጉ፣ ታገኛ ላችሁ፤ አንኳኩ፣ ይከፈትላችኋል።

፰ የሚለምን ሁሉ ይቀበላልና፣ እናም የሚፈልግም ያገኛል፤ እናም ለሚያንኳኩ ይከፈትላቸዋል።

፱ ወይም ከእናንተ ልጁ ዳቦ ቢለምነው ድንጋይ የሚሰጠው ማነው?

፲ ወይም ዓሳስ ቢለምነው እባብ ይሰጠ ዋልን?

፲፩ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ፣ ለልጆቻ ችሁ መልካም ስጦታ መስጠትን ካወቃ ችሁ፣ በሰማያት ያለው አባታችሁ ለሚ ለምኑት እንዴት አብልጦ መልካም ነገርን ይሰጣቸው?

፲፪ ስለሆነም፣ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተም ደግሞ እን ዲሁ [ሁ]አድርጉላቸው፣ ህግም ነቢያትም ይህ ነውና።

፲፫ [ሁ]በጠበበው ደጅ ግቡ፣ ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጅ ሰፊ መንገዱም [ሀ]ትልቅ ነውና፤ ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙ ናቸው፤

፲፬ ምክንያቱም ወደ ህይወት የሚወስደው [ሁ]ደጁ [ሀ]የጠበበ፣ መንገዱም የቀጠነ ስለሆነ፣ የሚያገኙትም ሓጥቂቶች ናቸው።

፲፭ የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባ ችሁ፣ ነገር ግን ውስጣቸው ነጣቂ ተኩላ ከሆኑ [ሁ]ከሀሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ።

፲፮ ከፍሬአቸው ታውቋቸዋላችሁ። ከእ

፴፫ ሀ ሉቃ. ፲፪፡ ፴፩።
፲፬ ፩ ሀ ጆ.ስት. ማቴ. ፯፡ ፩–፪ (ተጨማሪ)፤ ዮሐ. ፯፡ ፳፬።
፪ ሀ ሞር. ፰፡ ፲፱።
፭ ሀ ዮሐ. ፰፡ ፫–፲፩።
፮ ሀ ቅ.መ.መ. ቅዱስ።
፯ ሀ ፫ ኔፊ ፳፯፡ ፳፱።
ቅ.መ.መ. ጸሎት።
፲፪ ሀ ቅ.መ.መ. ርህራሄ።
፲፫ ሀ ሉቃ. ፲፫፡ ፳፬፤ ፫ ኔፊ ፳፯፡ ፴፫።
ለ ት.እና ቃ. ፲፴፪፡ ፳፭።
፲፩ ሀ ፪ ኔፊ ፱፡ ፶፭፤ ፴፭፤ ፱፡ ፲፪–፲፰፤ ት.እና ቃ. ፳፪።
ለ ፩ ኔፊ ፰፡ ፳።
ሐ ፩ ኔፊ ፲፱፡ ፲፪።
፲፭ ሀ ኤር. ፳፫፡ ፳፩–፴፪፤ ፪ ኔፊ ፳፰፡ ፱፣ ፲፪፡ ፲፭።

ሾህ ወይን፣ ወይም ከኩርንችትስ በለስ ይለ
ቀማልን?

፲፯ መልካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬን
ያፈራል፤ ክፉ ዛፍም መጥፎ ፍሬ ያፈራል።

፲፰ መልካም ዛፍ ክፉ ፍሬ ማፍራት፣
ወይንም ክፉ ዛፍ መልካም ፍሬን ማፍራት
አይቻለውም።

፲፱ መልካም ፍሬ ᵐየማያደርግ ዛፍ ሁሉ
ይቆረጣል፣ ወደ እሳትም ይጣላል።

፳ ስለዚህ፣ ᵐከፍሬአቸው ታውቋቸዋላ
ችሁ።

፳፩ በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ
የሚያደርግ እንጂ፣ ጌታ ሆይ፣ ጌታ ሆይ
የሚለኝ ሁሉ ወደ መንግስተ ሰማያት የሚ
ገባ አይደለም።

፳፪ በዚያ ቀን ብዙዎች ጌታ ሆይ፣ ጌታ
ሆይ፣ በስምህ ትንቢትን አልተናገርንምን፣
በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን፣ በስ
ምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን?
ᵐይሉኛል።

፳፫ እናም ከቶ ᵐአላውቃችሁም፣ እና
ንተ አመፀኞች፣ ከእኔ ᵃራቁ ብዬ አላው
ቃቸዋለሁ።

፳፬ ስለዚህ፣ ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያ
ደርገው ሁሉ፣ ቤቱን ᵐበአለት ላይ እንደ
ሰራ እንደ ጠቢብ ሰው አመሳስለዋለሁ—

፳፭ እናም ᵐዝናብ ወረደና፣ የጥፋት
ውሀም መጣ፤ እናም ነፋስ ነፈሰና፣ ቤቱን
ገፋው፤ እና ም በአለትም ላይ ስለተመሰረተ
ᵃአልወደቀም።

፳፮ እናም ይህንን ቃሌን ሰምቶ የማያደ
ርገው ሁሉ ቤቱን ᵐበአሸዋ ላይ እንደሰራ
ሰነፍ ሰው ይመሳሰላል—

፳፯ እናም ዝናቡ ወረደና፣ የጥፋት ውሀም
መጣ፣ እና ም ነፋሱ ነፈሰና፣ ቤቱን ገፋው፤
ወደቀና፣ አወዳደቁም ታላቅ ነበር።

ምዕራፍ ፲፭

*ኢየሱስ የሙሴ ህግ በእርሱ እንደተፈፀም
ተናገረ—ኔፋውያን በኢየሩሳሌም የተና
ገረላቸው ሌሎቹ በጎች ናቸው—በክፋ
ታቸው የተነሳ፣ በኢየሩሳሌም ያሉ የጌታ
ሰዎች ስለተበተኑት የእስራኤል በጎች አያ
ውቁም። ፴፬ ዓ.ም. ገደማ።*

፩ እናም እንግዲህ እንዲህ ሆነ ኢየሱስ
ንግግሩን በጨረሰ ጊዜ ዐይኑን በዙሪያው
ባሉ ሰዎች ላይ አሳረፈ፣ እናም እንዲህ
አላቸው፥ እነሆ ወደ አባቴ ከማረጌ በፊት
ያስተማርኩትን ነገሮች ሰምታችኋል፤
ስለዚህ፣ ይህንን ንግግሬን የሚያስታውስ
እናም ᵐየሚፈፅም በመጨረሻው ቀን ᵃአስ
ነሳዋለሁ።

፪ እናም እንዲህ ሆነ ኢየሱስ እነዚህን
ቃላት በተናገረ ጊዜ የሙሴን ᵐህግ በተመ
ለከተ ምን እንዲያደርጉ እንደሚፈልግባ
ቸው የሚገረሙና፣ የሚደነቁ ጥቂቶች እን
ዳሉ አስተዋለ፤ አሮጌዎቹ ነገሮች እንዳለፉ
እናም ሁሉም ነገሮች አዲስ እንደሆኑ የተነ
ገሩትን አልተረዱምና።

፫ እናም እንዲህ ሲል ተናገራቸው፥
አሮጌዎቹ ነገሮች አልፈዋል፣ እናም ሁሉም
ነገር አዲስ ሆነዋል ስላልኳችሁ አትገረሙ።

፬ እነሆ፣ ለሙሴ የተሰጠው ᵐህግ ተፈፅ
ሟል እላችኋለሁ።

፭ እነሆ፣ ህጉን የሰጠሁት ᵐእኔ ነኝ፤ ከእ
ስራኤል ህዝቦቼ ጋር ቃል ኪዳን የገባሁ
ትም እኔ ነኝ፤ ስለዚህ ህጉን ልፈጽም ስለ
መጣሁ ህጉ በእኔ ᵃተፈፅሟል፤ ስለዚህ
ይህም መጨረሻ አለው።

፮ እነሆ፣ ነቢያትን ᵐአልሽርም፣ ምክን
ያቱም ብዙዎች በእኔ አልተፈፀሙምና፣
እውነት እላችኋለሁ፣ ሁሉም ይፈፀማሉ።

፲፱ ᵐ ማቴ. ፫፡፲፣
አልማ ፭፡ ፴፯–፴፩፣
ት. እና ቃ. ፻፲፡ ፯።
፳ ᵐ ሉቃ. ፮፡ ፴፫–፴፭፣
ሞሮኒ ፯፡ ፭።
፳፪ ᵐ አልማ ፭፡ ፲፯።
፳፫ ᵐ ሞዛያ ፭፡ ፲፫፣ ፳፯፡ ፳፱–፳፯።
ᵃ ሉቃ. ፲፫፡ ፳፯።
፳፭ ᵐ ቅ.መ.መ. አለት።
፳፮ ᵐ አልማ ፳፯፡ ፯፣
ሔለ. ፭፡ ፲፪።
ᵃ ምሳ. ፲፪፡ ፯።
፳፯ ᵐ ፫ ኔፊ ፲፭፡ ፴።
፲፭ ፩ ᵐ ያዕ. ፩፡ ፳፪።
ᵃ ፩ ኔፊ ፲፫፡ ፴፯፣
ት. እና ቃ. ፭፡ ፴፭።
፪ ᵐ ቅ.መ.መ. የሙሴ ህግ።
፬ ᵐ ሞዛያ ፲፫፡ ፳፯–፴፩፣
፫ ኔፊ ፱፡ ፲፯–፳።
፭ ᵐ ፩ ቆሮ. ፲፡ ፩–፱፣
፫ ኔፊ ፲፩፡ ፲፱።
ቅ.መ.መ. ያህዌህ።
ᵃ አልማ ፴፱፡ ፲፫።
፮ ᵐ ፫ ኔፊ ፳፫፡ ፩–፭።

፲ እናም አሮጌዎቹ ነገሮች ያልፋሉ ስላ
ልኳችሁ፣ ስለሚመጡት ነገሮች ተነግረው
የነበሩትን አልሽርም።
፲፩ እነሆም፣ ከህዝቤ ጋር የገባሁት ᵐቃል
ኪዳን በሙሉ አልተፈጸመም፤ ነገር ግን
ለሙሴ የተሰጠው ህግ በእኔ መጨረሻ
አለው።
፲፪ እነሆ፣ እኔ ᵐህግ እንዲሁም ᵃብርሃን
ነኝ። ወደ እኔ ተመልከቱ፣ እናም እስከመ
ጨረሻው የጸናችሁ ሁኑ፣ እናም ᵐህያው
ትሆናላችሁ፤ እስከመጨረሻው ᵐለሚ
ፀናም የዘላለምን ህይወት እሰጠዋለሁና።
፲፫ እነሆ፣ ትዕዛዝን ሰጥቻችኋለሁ፤ ስለዚህ
ᵐትዕዛዜን ጠብቁ። እናም ህጉና ነቢያትም
ይህ ነው፣ ስለእኔ በእውነት ᵃይመሰክራሉና።
፲፬ እናም እንግዲህ እንዲህ ሆነ ኢየሱስ
እነዚህን ቃላት በተናገረበት ጊዜ፣ ለእነ
ዚያ ለመረጣቸው አስራ ሁለቱ እንዲህ አላ
ቸው፥
፲፭ እናንተ የእኔ ደቀመዛሙርት ናችሁ፤
እናም ᵐለዮሴፍ ቤት ቅሪት ለሆኑትም ለእ
ነዚህ ሰዎች ብርሃን ናችሁ።
፲፮ እናም እነሆ፣ ይህች ᵐምድር የርስታ
ችሁ ስፍራ ናት፣ እናም አብም ለእናንተ
ይህን ሰጥቷችኋል።
፲፯ እናም በኢየሩሳሌም ለሚገኙት ወንድ
ሞቻችሁ በማንኛውም ጊዜ ይህን ᵐእንድና
ገር አብ ትዕዛዝ አልሰጠኝም ነበር።
፲፰ አብ ከምድሪቱ እንዲወጡ ስለመራ
ቸው የእስራኤል ቤት ስለሆኑት ᵐሌሎች ነገ
ዶች በየትኛውም ጊዜ በኢየሩሳሌም ላሉት
ወንድሞቻችሁ እንድናገር ትዕዛዝ አልሰ
ጠኝም።
፲፱ አብም እስከዚህ ድረስ ለእነርሱ እን
ድናገራቸው አዞኛል፥
፲፲ ከዚህም በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች
አሉኝ፤ እነርሱንም ደግሞ ላመጣ ይገባ
ኛል፣ ድምፄንም ይሰማሉ፣ አንድም መንጋ
ይሆናሉ፣ ᵐእረኛውም አንድ ይሆናል።
፲፲ እናም እንግዲህ፣ አንገተ ደንዳና በመ
ሆናቸውና፣ ባለማመናቸው ቃሌን ᵐሊረዱ
አልቻሉም፤ ስለዚህ ይህን ነገር በተመለ
ከተ ከዚህ የበለጠ እንዳልናገር በአብ ታዝዜ
ነበር።
፲፲ ነገር ግን፣ እውነት እላችኋለሁ፣ በክ
ፋታቸው የተነሳ እናንተ ከእነርሱ ተለይታ
ችኋል ብዬ እነግራችሁ ዘንድ አብ አዞኛል፤
ስለዚህ በክፋታቸውም የተነሳ ነው ስለእና
ንተ የማያውቁት።
፲፳ እናም እንደገና እውነት እላችኋለሁ፣
ሌሎች ነገዶችን አብ ከእነርሱ ለይቷል፤
እናም በክፋታቸው የተነሳ ነው ስለእነርሱ
የማያውቁት።
፲፳፩ እናም እውነት እላችኋለሁ፤ ከዚህም
በረት ያልሆኑ ᵐሌሎች በጎች አሉኝ፤ እነ
ርሱን ደግሞ ላመጣ ይገባኛል፤ እነርሱም
ድምጼን ይሰማሉ፤ እናም አንድ መንጋና፣
እረኛውም አንድ ይሆናል፣ በማለት የተና
ገርኩአችሁ እናንተ ናችሁ።
፲፳፪ እናም ሌሎቹ በጎች ᵐአህዛብ ናቸው
ብለው ስለገመቱ እኔን አልተረዱኝም፤
ምክንያቱም አህዛብ በእነርሱ ስብከት ᵃእን
ደሚለወጡ አልተረዱምና።
፲፳፫ እናም ድምፄን ያዳምጣሉ ማለቴ
ንም አልተረዱም፤ እናም በማንኛውም
ጊዜ ᵐአህዛብ ድምፄን መስማት እንደማይ
ችሉ፣ ᵃበመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ካል
ሆነም በቀር ራሴን እንደማልገልፅላቸውም
አልተረዱኝም።
፲፳፬ ነገር ግን እነሆ፣ ᵐድምፄን ሰምታችኋ

፲፰ ሀ ቮ ኔፊ ፭፡፲፳–፲፳፮።
፲፱ ሀ ፪ ኔፊ ፲፮፡፩።
ለ ቅ.መ.መ. ብርሀን፣ የክርስቶስ
ብርሀን።
ሐ ዮሐ. ፲፭፡፲፳፤
ት. እና ቃ. ፹፬፡፬–፱፡
መ ቅ.መ.መ. መፅናት።
፲ ቮ ኔፊ ፲፪፡፲፳።
ለ ሞዛያ ፲፫፡ ፴፫።
፲፪ ሀ ቅ.መ.መ. ዮሴፍ፣ የያዕቆብ
ልጅ።
፲፫ ሀ ፩ ኔፊ ፲፡፡፲፳–፲፫።
፲፬ ሀ ቮ ኔፊ ፭፡፲፳።
፲፭ ሀ ቮ ኔፊ ፲፮፡፩–፬።
ቅ.መ.መ. እስራኤል—
የጠፉት የእስራኤል አስር
ጎሳዎች።
፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. መልካሙ እረኛ።
፲፡ ሀ ት. እና ቃ. ፲፡ ፶፱።
፲፱ ሀ ዮሐ. ፲፡ ፲፬–፲፯።
፲፱ ሀ ቅ.መ.መ. አህዛቦች።
ለ የሐዋ. ፲፡ ፴፬–፴፭።
፲፫ ሀ ማቴ. ፲፭፡ ፲፬።
ለ ፩ ኔፊ ፲፡ ፲፩።
ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
፲፳ ሀ አልማ ፭፡ ፴፡፡
ቮ ኔፊ ፲፯፡ ፩–፭።

ልም፣ አይታችሁኛልም፤ እናንተም የእኔ በጎች ናችሁ፤ እናም አብ ለእኔ ^ከሰጣቸው መካከልም የተቆጠራችሁ ናችሁ።

ምዕራፍ ፲፤

ኢየሱስ ሌሎችን የጠራቸውን የእስራኤል በጎች ይጎበኛቸዋል—በኋለኛው ቀን ወን ጌል ለአህዛብ እናም ወደ እስራኤል ቤት ይሄዳል—እግዚአብሔር ፅዮንን ዳግም በሚመልስበት ጊዜ የጌታ ሰዎች ዐይን ለዐ ይን ይተያያሉ። ፴፩ ዓ.ም. ገደማ።

፩ እናም እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ከዚህች ምድር ወይም ከኢየሩሳሌም ወይም እኔ ካገለገልኩባቸውም ቦታዎች ዙሪያ ያል ሆኑ ^ሌሎች በጎች አሉኝ።

፪ የምናገርባቸውም ገና ድምፄን አልሰ ሙትምና፤ ወይም በማንኛውም ጊዜ ራሴን አልገለጽኩላቸውም።

፫ ነገር ግን ወደ ^እነርሱ እንድሄድ ዘንድ፣ እናም ድምፄን ይሰሙና፣ ከበጎቼም ጋር ይቆጠሩ፣ እናም አንድም መንጋ፣ እረኛ ውም አንድ እንዲሆን ከአብ ትዕዛዝ ተቀብያ ለሁ፤ ስለዚህ ራሴንም ላሳያቸው እሄዳለሁ።

፬ እናም እኔም ከሄድኩኝ በኋላ ይህንን ^የተናገርኩትን እንድትፅፉ አዛችኋለሁ፤ ይህ ከሆነ እኔን የተመለከቱኝና፣ በአገል ግሎቴ ወቅት ከእኔ ጋር የነበሩት በኢየሩ ሳሌም ያሉት ህዝቦቼ ስለ እናንተ፣ እናም ደግሞ ስለሚያውቋቸው ሌሎች ነገዶች በመንፈስ ቅዱስ እውነትን ያገኙ ዘንድ አብን በስሜ ካልጠየቁ፣ በዚህም ^በአህዛብ ሙላት በኩል፣ ባለማመናቸው ምክንያት በምድር ገፅ ላይ የሚበተኑት የዘሮቻቸው ቅሪት እንዲመጡ ዘንድ፣ ወይም አዳኛቸው ወደሆንኩት ወደ እኔም ^እውቀት ይመጡ ዘንድ እናንተ የምትፅፏቸው እነዚህ አባባ ሎች ይጠበቃሉ እና ለአህዛብም ይገለጻሉ።

፭ እናም ከምድሪቱ ከአራቱም ማዕዘናት ^እሰበስባቸዋለሁ፤ እናም አብ ^ከእስራኤል ቤት ከሁሉም ጋር የገባውን ^ቃል ኪዳን እፈፅማለሁ።

፮ እናም ^አህዛብ ስለእኔ እንዲሁም ስለ እኔና ስለአብ ስለሚመሰክርላቸው ^መን ፈስ ቅዱስ በማመናቸው የተባረኩ ናቸው።

፯ እነሆ፣ አብም እንዲህ ይላል፣ በእኔም ስለሚያምኑ፣ እናም፣ የእስራኤል ቤት ሆይ፣ እናንተ ስለማታምኑ ^በኋለኛው ቀን እውነት ለአህዛብ ትመጣለች፤ የእነ ዚህን ነገሮች ሙሉነት እነርሱ እንዲያው ቁት ይሆናል።

፰ ነገር ግን አብም ለማያምኑ አህዛብ ወዮ ላቸው ይላል—እነርሱ ወደዚህች ምድር ገፅ የመጡም ቢሆኑ፣ እናም የእስራኤል ቤት የሆኑትንም ህዝቦቼን ^ቢበትኑም፣ እናም ከእስራኤል ቤት የሆኑት ህዝቦቼ ከመካከ ላቸው ^ቢጣሉም፣ እናም በእነርሱም እግር ቢረገጡም፤

፱ እናም አብ ለአህዛብ ባለው ምህረቱና፣ ደግሞ የእስራኤል ቤት በሆኑት ህዝቦቼ ላይ በአብ በነበረው ቅጣት የተነሳ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ከዚህ ሁሉ በኋላ፣ እናም የእስራኤል ቤት የሆኑትን ህዝቦቼን እንዲመቱና፣ እንዲሰቃዩ፣ እናም ^እን ዲገለሉና፣ ከመካከላቸው እንዲጣሉም፣ በእነርሱ እንዲጠሉና፣ በአህዛብ መካከል እንዲያፏጭባቸው እናም እንዲናቁ ካደ ረኩኝ በኋላ—

ሀ ፩ ዮሐ. ፤ ፡ ፴፯፤ ት. እና ቃ. ፰፤ ፡ ፲፬።
፲፤ ፩ ሀ ፫ ኔፊ ፲፭ ፡ ፲፭። ቅ.መ.መ. እስራኤል—የጠፉት የእስራኤል አስር ጎሳዎች።
፫ ሀ ፫ ኔፊ ፲፯ ፡ ፴። ፬ ሀ ቅ.መ.መ. ቅዱሳት መጻህፍት።
ለ ፩ ኔፊ ፣ ፡ ፲፴፤ ፫ ኔፊ ፳፩ ፡ ፤። ሐ ሕዝ. ፳ ፡ ፵፪–፵፬፤ ፫ ኔፊ ፳ ፡ ፲፫። ፭ ሀ ቅ.መ.መ. እስራኤል—የእስራኤል መሰብሰብ።
ለ ፩ ኔፊ ፳፪ ፡ ፱፤ ፫ ኔፊ ፳፩ ፡ ፳፯–፳፱። ሐ ፫ ኔፊ ፭ ፡ ፳፬–፳፯። ፯ ሀ ፩ ኔፊ ፲፫ ፡ ፴–፴፪፤ ፪ ኔፊ ፴ ፡ ፫።
ለ ፪ ኔፊ ፴፪ ፡ ፭፤ ፫ ኔፊ ፲፩ ፡ ፴፪፣ ፴፭–፴፯። ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ። ፯ ሀ ቅ.መ.መ. የወንጌል ዳግም መመለስ። ፰ ሀ ፩ ኔፊ ፲፫ ፡ ፲፬፤ ሞር. ፭ ፡ ፱፣ ፲፭። ለ ፫ ኔፊ ፳ ፡ ፳፯–፳፱። ፱ ሀ ዓም. ፱ ፡ ፩–፭።

፲ እናም እንዲህ እንድላችሁም አብ አዞ
ኛል፥ አህዛብ በዚያ ቀን በወንጌሴ ላይ ኃጢ
ያት ሲፈፅሙ፣ እናም የወንጌሌንም ሙሉ
ነት አንቀበልም ሲሉና፣ ልባቸው ከሀገር
ሁሉ በላይ፣ እናም በምድሪቱ ካሉት ሰዎች
ሁሉ በላይ ልባቸው በኩራት ሀሲወጠር፣
እናም በሁሉም አይነት ውሸትና፣ በማጭ
በርበርም፣ በግብዝነትም፣ በመግደልም፣
ለበካህናት ተንኮልና በዝሙት፣ እናም በሚ
ስጥር እርኩሰት የተሞሉ ሲሆኑ፤ እናም እነ
ዚህን ነገሮች በሙሉ የሚያደርጉ ከሆነና
የወንጌሌን ሙሉነት ካልተቀበሉ፣ እነሆ፣
አብ እንዲህ ይላል፣ የወንጌሌን ሙሉነት
ከመካከላቸው እወስድባቸዋለሁ።
፲፩ እና ከዚያም፣ የእስራኤል ቤት ሆይ፣
ለህዝቤ የገባሁትን ቃል ኪዳን ሀአስታው
ሳለሁ፣ እናም ወንጌሌንም ለእነርሱ አመ
ጣለሁ።
፲፪ እናም የእስራኤል ቤት ሆይ፣ አህዛብ
በእናንተ ላይ ስልጣን እንደሌላቸው አሳ
ያችኋለሁ፤ ነገር ግን የእስራኤል ቤት ሆይ
ለእናንተ የገባሁትን ቃል ኪዳን አስታው
ሳለሁ፣ እናም ወደ ወንጌሌ ሙሉ ሀእውቀ
ትም ትመጣላችሁ።
፲፫ ነገር ግን አብም እንዲህ ይላል፥ አህ
ዛብ ንሰሃ ከገቡ፣ እናም ወደ እኔ ከተመ
ለሱ፣ የእስራኤል ቤት ሆይ፣ ከህዝቦቼ መካ
ከል ሀየተቆጠሩ ይሆናሉ።
፲፬ እናም አብም እንዲህ ይላል፥ የእስራ
ኤል ቤት የሆኑትን ህዝቦቼን በመካከላቸው
አልፈው እናም እንደ ጭቃ እንዲረግጧ
ቸው አልፈቅድም።
፲፭ ነገር ግን ወደ እኔ ካልተመለሱና፣
ድምፄን ካልሰሙ፣ እነርሱን አዎን፣ የእ
ስራኤል ቤት የሆኑት ህዝቦቼ ወደ እነርሱ
እንዲሄዱና፣ እንደጭቃም እንዲረግጧ
ቸው እፈቅዳለሁ፣ እናም ጣዕሙን እን
ዳጣ ጨውም ሆነው፣ ከዚህ ጊዜ በኋላ ከንቱ
እንደሆኑ ነገር ግን እንደሚወረወሩ፣ እናም
የእስራኤል በሆኑትም በህዝቦቼ ሀየሚረገጡ
ይሆናሉ።
፲፮ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ—ለዚህ
ህዝብ ይህንን የርስት ምድራቸውን እንድ
ሰጣቸው አብ እኔን አዞኛል።
፲፯ እናም ነቢዩ ኢሳይያስም እንዲህ ሲል
የተናገራቸው ሀቃላት ይፈጸማሉ፥
፲፰ ሀየአንቺ ለጠባቂዎች ይጮሀሉ፤
ጌታም ወደ ፅዮን በተመለሰ ጊዜ፣ ዐይን
ለዐይን ይተያያሉና፣ በአንድነት ድምጽም
ይዘምራሉ።
፲፱ እናንተ የኢየሩሳሌም ፍርስራሾች፣
ጌታ ህዝቡን አፅናንቶአልና፤ ኢየሩሳሌ
ምን ታድጎአልና ደስ ይበላችሁ፣ በአንድ
ነትም ዘምሩ።
፳ ጌታም የተቀደሰውን ክንዱን በሀገሮች
ሁሉ ፊት ገልጧል፤ እናም በምድር ዳርቻም
ያሉት ሁሉ የእግዚአብሔርን መድሐኒት
ያያሉ።

ምዕራፍ ፲፯

ኢየሱስ ህዝቡ ስለቃሉ እንዲያገናዝቡ እናም እንዲፀልዩ አዘዘ—በሽተኞቻቸውን ፈወሰ—ለመፃፍ በማይቻል ቋንቋ ስለህዝቡ ፀለየ—ህፃናቶቻቸውን መላዕክት አስተማሩአቸው እናም በእሳት ተከበቡ። ፴፬ ዓ.ም. ገደማ።

፩ እነሆ፣ እንግዲህ እንዲህ ሆነ ኢየሱስ
እነዚህን ቃላት በተናገረ ጊዜ ወደ ህዝቡ
በድጋሚ ዙሪያውን ተመለከተ፤ እናም
እንዲህ ሲል ተናገራቸው፥ እነሆ ሀጊዜዩ
ቀርቦአል።

፲ ሀ ሞር. ፰፥፴፰–፵፩።
ለ ፪ ኔፊ ፳፮፥፳፱።
፲፩ ሀ ፫ ኔፊ ፳፩፥፩–፲፩፤
ሞር. ፳፥፳።
፲፪ ሀ ሔለ. ፲፭፥፲፪–፲፫።
፲፫ ሀ ገላ. ፫፥፯፣ ፳፱፤
፩ ኔፊ ፲፭፥፲፫–፲፯፤
፪ ኔፊ ፲፥፲፰፤ ፫ ኔፊ ፴፥፪፤
አብር. ፪፥፱–፲፩።
፲፭ ሀ ሚክ. ፭፥፰–፲፭፤
፫ ኔፊ ፳፥፲፮–፲፱፤
፳፩፥፲፪–፳፩፤
ት. እና ቃ. ፹፯፥፭።
፲፯ ሀ ፫ ኔፊ ፳፥፲፩–፲፪።
፲፰ ሀ ኢሳ. ፶፪፥፰–፲።
ለ ሕዝ. ፴፫፥፩–፯።
ቅ.መ.መ. መጠበቅ፣
ጠባቂ።
፲፯ ፩ ሀ ይህም ወደ አብ መመለስ
ማለት ነው። ቁጥር ፬ን
ተመልከቱ።

፪ በዚህ ጊዜ በአባቴ ለእናንተ እንድናገር የታዘዝኩትን ቃሌን በሙሉ ልትረዱ እን ደማትችሉ ደካሞች መሆናችሁን ᵐአስተ ውላለሁ።

፫ ስለዚህ፣ ወደቤታችሁ ሂዱና፣ ስለ ተናገርኳችሁ ነገሮች ᵐአሰላስሉ፤ እናም ትረዱና ᵃለሚቀጥለው ቀን አእምሮአች ሁን ᵐታዘጋጁ ዘንድ በስሜ አብን ጠይቁት፣ እናም እኔም በድጋሚ እመጣለሁ።

፬ ነገር ግን አሁን ወደ አባቴ፣ እናም ደግሞ ራሴን ᵐለጠፉት የእስራኤል ነገዶች ᵃለማሳ የት ᵐእሄዳለሁ፤ ምክንያቱም እነርሱ ለአብ አልጠፉምና፣ እርሱም የት እንደወሰዳቸው ያውቃልና።

፭ እናም እንዲህ ሆነ ኢየሱስ እንዲህ በተናገረ ጊዜ፣ ዐይኑን በድጋሚ በህዝቡ ላይ በዙሪያው ያደርግ ነበር፤ እናም እንባ እያነቡ መሆናቸውንና፣ እርሱ ከእነርሱ ጋር ትንሽ እንዲቆይ የሚፈልጉ በመምሰል በእ ርሱ ላይ ያተኮሩ ይመስሉ እንደነበር ተመ ለከተ።

፮ እናም እርሱ እንዲህ አላቸው፥ እነሆ፣ ስለእናንተ አንጀቴ ᵐበርህራሄ ተሞልቷል።

፯ ከእናንተ መካከል በሽተኞች አሉን? ወደዚህ ስፍራ አምጡአቸው። ከእናንተ መካከል ድውይ፣ ወይንም ዐይነስውር፣ ወይንም ሽባ፣ ወይንም ለምፃም፣ ወይንም ሰውነታቸው የሰለለ፣ ወይንም ደንቆሮ፣ ወይንም በተመሳሳይ የሚሰቃዩ አሉን? ወደ እዚህ ስፍራ አምጡአቸው እናም ለእናንተ ከአንጀቴ ርህራሄ ስላለኝ እፈውሳቸዋለሁ፤ ውስጤም በምህረት ተሞልቷል።

፰ በኢየሩሳሌም ለነበሩት ወንድሞቻችሁ ምን እንዳደረግሁ እንዳሳያችሁ እንደምት ፈልጉ እገነዘባለሁ፣ ምክንያቱም እናንተን እንድፈውሳችሁ ᵐእምነታችሁ ᵃበቂ መሆ ኑን አይቻለሁና።

፱ እናም እንዲህ ሆነ ይህንን በተናገረ ጊዜ፣ ህዝቡ በሙሉ በአንድ ልብ ከበሽተኞ ቻቸው፣ እንዲሁም ከሚሰቃዩትና፣ ከሽባ ዎቹ፣ እናም ከዐይነ ስውሮቹና፣ ከዲዳዎ ቹና፣ በሁሉም ዐይነት በሽታ ከሚሰቃዩ ሰዎች ጋር ሄዱ፤ እናም ወደ እርሱም በቀ ረቡ ጊዜ እያንዳንዳቸውን ᵐፈወሳቸው።

፲ እናም እነርሱም በሙሉ፣ የተፈወሱ ትም ሆኑ ጤነኛዎቹ፣ በእግሩ ስር ሰገዱና፣ አመለኩት፤ እናም በእንባቸው እግሩ እስከ ሚታጠብ ድረስ ብዙዎች ወደ እርሱ ቀር በው ᵐእግሩን ሳሙት።

፲፩ እናም እንዲህ ሆነ ᵐህፃናት ወደ እርሱ እንዲመጡ አዘዘ።

፲፪ ስለዚህ ህፃናት ልጆቻቸውን አመጡና በእርሱ ዙሪያም አስቀመጡአቸው፣ እናም ኢየሱስ በመካከላቸው ቆመ፤ እናም ህፃ ናት በሙሉም ወደ እርሱ እንዲቀርቡ ህዝቡ ቦታ ለቀቀ።

፲፫ እናም እንዲህ ሆነ ሁሉም በመጡ ጊዜ፣ እናም ኢየሱስ በመካከላቸው በቆመ ጊዜ ህዝቡ በመሬት ላይ ᵐእንዲንበረከክ አዘዘ።

፲፬ እናም እንዲህ ሆነ በመሬት ላይ በተን በረከኩም ጊዜ፣ ኢየሱስም በውስጡ እን ዲህ ሲል ቃተተ፥ አባት ሆይ የእስራኤል ቤት በሆኑት ሰዎች ኃጢያት ᵐአዝኜአለሁ።

፲፭ እናም እነዚህን ቃላት በተናገረ ጊዜ እርሱም ደግሞ በመሬት ላይ ተንበረከከ፤ እናም እነሆ ወደ አብ ፀለየ፣ የፀለየባቸውም ነገሮች ምንም ሊፃፉ አይቻሉም፣ የሰሙ ትም ሰዎች መስክረዋልም።

፲፮ እናም በዚህም ሁኔታ መስክረዋል፥ ከዚህ በፊት ዐይን ᵐያላየውን፣ ጆሮም ያል

፪ ሀ ዮሐ. ፲፮፡ ፲፪፡
ት. እና ቃ. ፫፯፡ ፲፯–፲፰።
፫ ሀ ቅ.መ.መ. ማሰላሰል።
ለ ፫ ኔፊ ፲፱፡ ፪።
ሐ ት. እና ቃ. ፻፴፪፡ ፫።
፬ ሀ ቅ.መ.መ. እስራኤል—
የጠፉት የእስራኤል አስር
ነሳዎች።
ለ ፫ ኔፊ ፲፮፡ ፩–፫።
ሐ ፫ ኔፊ ፲፭፡ ፴፱።
፮ ሀ ቅ.መ.መ. ርህራሄ።
፯ ሀ ሉቃ. ፲፭፡ ፣፪።
ለ ፪ ኔፊ ፳፮፡ ፳፫፤
ኤተር ፲፪፡ ፲፪።
፱ ሀ ሞዛያ ፫፡ ፭፤
፫ ኔፊ ፳፯፡ ፲፭።
፲ ሀ ሉቃ. ፯፡ ፴፰።
፲፩ ሀ ማቴ. ፲፱፡ ፲፫–፲፬፤
፫ ኔፊ ፳፯፡ ፲፡ ፲፯።
፲፫ ሀ ሉቃ. ፳፪፡ ፲፡
የሐዋ. ፯፡ ፴፯።
፲፬ ሀ ሙሴ ፯፡ ፣፴፩።
፲፯ ሀ ኢሳ. ፳፡ ፣፡
፩ ቆሮ. ፪፡ ፣፣
ት. እና ቃ. ፫፯፡ ፲፡
፣፣፲–፣፣፲፱።

ሰማውን፤ ኢየሱስ ወደ አብ ሲናገር ያየ ናቸው እናም የሰማናቸው ነገሮች ታላቅና አስደናቂ ነገሮችን ነው፤

፲፯ እናም ᵐአንደበት ሊናገረው አይች ልም፣ እንዲሁም በማንም ሰው ሊፃፍ አይ ችልም፤ ኢየሱስ ሲናገር እኛ እንዳየናቸውና እንደሰማናቸው ያሉ ታላቅና አስደናቂ ነገ ሮች የሰው ልብ ሊገምተው አይቻለውም፤ እናም ወደ አብ ለእኛ ሲፀልይ በሰማነው ጊዜ ነፍሳችን የተሞላችበትን ዐይነት ደስታ ማንም ሊገምተው አይቻለውም።

፲፰ እናም እንዲህ ሆነ ኢየሱስ ወደ አብ መፀለይን በጨረሰ ጊዜ ተነሳ፤ ነገር ግን የህዝቡ ᵐደስታ ታላቅ ስለነበረ እነደተሸ ነፉም ሆኑ።

፲፱ እናም እንዲህ ሆነ ኢየሱስ ተናገራቸ ውና፣ እንዲነሱ አዘዛቸው።

፳ እነርሱም ከመሬቱ ላይ ተነሱ፤ እናም እንዲህ ሲል ተናገራቸው፥ እናንተ በእም ነታችሁ የተባረካችሁ ናችሁ። እናም እን ግዲህ እነሆ፣ ደስታዬ ሙሉ ነው።

፳፩ እናም እነዚህን ቃላት በተናገረ ጊዜ ᵐአለቀሰ፤ ህዝቡም ስለማልቀሱ መሰከሩ፣ አንድ በአንድም ህፃናቶቻቸውን ወሰዳቸ ውና፣ ᵃባረካቸውም፣ ስለእነርሱም ወደ አብ ፀለየ።

፳፪ እናም ይህንንም ሲያደርግ በድጋሚ አለቀሰ፤

፳፫ እናም ለህዝቡ ተናገረና፣ እንዲህ አላ ቸው፥ ህፃናቶቻችሁን ተመልከቱ።

፳፬ እናም ለመመልከት ዐይኖቻቸውን በሰማይ ላይ አደረጉና፣ ሰማያት ሲከፈቱ ተመለከቱ፣ እናም መላዕክቱ ልክ በእሳት መካከል እንደሆነ ከሰማይ ሲወርዱ ተመ ለከቱ፤ እነርሱም ወርደው ህፃናቱን ᵐከበቡ አቸው፣ በእሳቱም ተከበቡ፤ እናም መላዕ ክት አገለገሉአቸው።

፳፭ እናም ህዝቡ ተመለከቱና ሰሙ እናም መሰከሩ፤ ሁሉም እያንዳንዱ ለራሱ ስለተ መለከተና ስለሰማ ምስክርነታቸውም እው ነት መሆኑን ያውቃሉ፤ እናም በቁጥርም ሁለት ሺህ አምስት መቶ ነፍሳት ገደማ ነበሩ፤ እነርሱም ወንዶች፣ ሴቶችና፣ ህፃ ናት ነበሩ።

ምዕራፍ ፲፰

ኢየሱስ በኔፋውያን መካከል ቅዱስ ቁርባ ንን ᵖመረ—ሁል ጊዜም በስሙ እንዲጸ ልዩ ታዘዙ—ብቁ ሳይሆኑ ስጋውን የሚበሉ እናም ደሙን የሚጠጡ ይኮነናሉ—ደቀ መዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስን እንዲሰጡ ስልጣን ተሰጣቸው። ፭፩ ዓ.ም. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ ኢየሱስ ደቀመዛሙ ርቱ ጥቂት ᵐዳቦ እና ወይን ወደ እርሱ እን ዲያመጡ አዘዛቸው።

፪ እና እነርሱ ዳቦውንና ወይኑን ለማም ጣት በሄዱበት ጊዜ፣ ህዝቡን በመሬት ላይ እንዲቀመጡ አዘዘ።

፫ እናም ደቀመዛሙርቱ ᵐዳቦውንና ወይ ኑን ይዘው በመጡ ጊዜ፣ ከዳቦው ወስዶ በመቁረስ ባረከው፤ እናም ለደቀመዛሙ ርቱም ሰጣቸውና እንዲበሉትም አዘዛቸው።

፬ እናም በበሉና በተሞሉ ጊዜ፣ ለህዝቡ እንዲሰጡ አዘዘ።

፭ እናም ህዝቡም በልተው በተሞሉ ጊዜ፣ ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ አላቸው፥ እነሆ ከመካከላችሁ አንዱ ይሾማል፤ እናም በስሜ ለሚያምኑትና ለሚጠመቁት ለቤ ተክርስቲያኔ ህዝቦች ዳቦውን ᵐእንዲቆር ሰውና በመባረክ እንዲሰጣቸው ስልጣንን እሰጠዋለሁ።

፮ እናም እኔ እንዳደረግሁትም ቢሆን፣ እንዲሁም እኔም ዳቦውን እንደቆረስኩ ትና እንደባረክሁት እናም ለእናንተ እን ደሰጠኋችሁ ይህንን ሁል ጊዜ በቀጣይነት አድርጉ።

፯ እናም ይህንን ያሳየኋችሁን ስጋዬን

፲፯ *ሀ* ፪ ቆሮ. ፲፪፡፬።
፲፰ *ሀ* ቅ.መ.መ. ደስታ።
፳፩ *ሀ* ዮሐ. ፲፩፡ ፴፮።
ለ ማር. ፲፡ ፲፩–፲፮።
፳፩ *ሀ* ሐሌ. ፭፡ ፳፫–፳፬፣ ፴፫–፴፭።
፲፰ ፩ *ሀ* ማቴ. ፳፮፡ ፳፮–፳፰።
ቮ *ሀ* ቅ.መ.መ. ቅዱስ ቁርባን።
፭ *ሀ* ሞሮኒ ፩።

ᵐለማስታወስ አድርጉ። ይህም ሁልጊዜ
እኔን እንደምታስታውሱ ለአብ ለምስክር
ነት ይሆናል። እናም ሁልጊዜ የምታስታው
ሱኝ ከሆነ መንፈሴ ከእናንተ ጋር ይሆናል።
፳ እናም እንዲህ ሆነ እነዚህን ቃላት በተ
ናገረ ጊዜ፣ ደቀመዛሙርቱን ከወይኑ በጥ
ቂቱ እንዲወስዱና ከፅዋውም እንዲጠጡ፣
እናም ደግሞ ህዝቡም ይጠጡ ዘንድ እንዲ
ሰጡአቸው አዘዛቸው።
፳፩ እናም እንዲህ ሆነ የተባሉትን አደረጉ፣
ከዚህም ጠጡና ተሞሉ፤ ለህዝቡም ሰጡ፣
እናም እነርሱም ጠጡና ተሞሉ።
፲ እናም ደቀመዛሙርቱም ይህንን ባደ
ረጉ ጊዜ ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፥ ስላደ
ረጋችሁት ስለእነዚህ ነገሮች ተባርካችኋል፤
ምክንያቱም ይህ ትዕዛዛቴን መፈፀም ነው፣
እናም ይህም ያዘዝኳችሁን ለመፈፀም ፈቃ
ደኞች መሆናችሁን ለአብ ይመሰክራል።
፲፩ እናም ይህን ንሰሃ ለገቡትና በስሜ ለተ
ጠመቁት ሁልጊዜ ታደርጉታላችሁ፣ እናም
ይህንንም ለናንተ ያፈሰስኩትን ደም ለማ
ስታወስ፤ እኔን ሁልጊዜ እንደምታስታው
ሱኝ ለአብ ለመመስከር ታደርጉታላችሁ።
እናም ሁልጊዜም የምታስታውሱኝ ከሆነ
መንፈሴ ከእናንተ ጋር ይሆናል።
፲፪ እናም እነዚህን ነገሮች እንድታደርጉ
ትዕዛዛትን እሰጣችኋለሁ። እናም እነዚህን
ነገሮች ሁል ጊዜ የምታደርጉ ከሆነ፣ የተ
ባረካችሁ ናችሁ፣ ᵐበአለት ላይ ቤታችሁን
ሰርታችኋልና።
፲፫ ነገር ግን ከእናንተ መካከል ከዚህ የበለ
ጠም ሆነ ያነሰ የሚሰራ፣ በአለቱ ላይ ቤቱን
አልሰራም፣ ነገር ግን በአሸዋ ላይ መሰረቱን
ሰርቷል፤ እናም ዝናብ በሚወርድበትና የጥ
ፋት ውሀ በሚመጣበት፣ እናም ነፋስ በሚ
ነፍስበትና፣ በሚመታቸው ጊዜ ᵐይወድ
ቃሉ፣ እናም የገሃነም ᶮደጆችም እነርሱን
ለመቀበል ክፍት ይሆናሉ።
፲፬ ስለዚህ ለእናንተ እንድሰጣችሁ አብ
ያዘዘኝን ትዕዛዛት የምትጠብቁ ከሆነ እና
ንተ የተባረካችሁ ናችሁ።
፲፭ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ዘወ
ትር ንቁ መሆን እና ᵐመፀለይ አለባችሁ፤
አለበለዚያ በዲያብሎስ ትፈተናላችሁ
እናም የእርሱ ምርኮኛም ትሆናላችሁ።
፲፮ እናም በመካከላችሁ እንደጸለይኩት
እናንተም ንሰሃ በገቡትና በስሜ በተጠ
መቁት ህዝቦቼ መካከል በቤተክርስቲያኔ
በተመሳሳይ ፀልዩ። እነሆ እኔ ᵐብርሃን ነኝ፤
ᶮምሳሌም ትቼላችኋለሁ።
፲፯ እናም እንዲህ ሆነ ኢየሱስ ለደቀመዛ
ሙርቱ እነዚህን ቃላት በተናገረ ጊዜ፣ ወደ
ህዝቡ በመዞር እንዲህ ሲል ተናገራቸው፥
፲፰ እነሆ፣ እውነት፣ እውነት እላችኋ
ለሁ፣ እንዳትፈተኑ ዘወትር መንቃት እናም
መፀለይ አለባችሁ፤ ምክንያቱም ᵐሰይጣን
እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ይፈልጋችኋ
ልና።
፲፱ ስለዚህ ዘወትር በስሜ ወደ አብ መፀ
ለይ ይኖርባችኋል፤
፳ እናም በስሜ ትክክል የሆነውን ᵐማን
ኛውንም ነገር በእምነት እናገኛለን በማለት
አብን ከጠየቃችሁት፤ እነሆ ለእናንተ ይሰ
ጣችኋልና።
፳፩ ሚስቶቻችሁ እና ልጆቻችሁ ይባ
ረኩ ዘንድ፣ ዘወትር ከቤተሰቦቻችሁ ጋር
በስሜ ᵐፀልዩ።
፳፪ እናም እነሆ፣ ዘወትር በአንድነት ተሰ
ባሰቡ፣ እናም በአንድነት በምትሆኑበት ጊዜ
ማንም ሰው ወደእናንተ እንዳይመጣ አትከ
ልክሉ፤ ነገር ግን ወደ እናንተ ይመጡ ዘንድ
ፍቀዱላቸውና አትከልክሉአቸው፤

፲ ᵐ ሞሮኒ ፪፡፫፤
፲፪ ᵐ ቅ.መ.መ. አለት።
፲፫ ᵐ ቅ.መ.መ. ክህደት።
ᶮ ፫ ኔፊ ፲፭፡፴፱።
፲፭ ᵐ አልማ ፴፡፣ ፲፯–፳፯።
ቅ.መ.መ. ጸሎት።
፲፯ ᵐ ቅ.መ.መ. ብርሀን፣ የክርስቶስ
ብርሀን።
ᶮ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ
ክርስቶስ—የኢየሱስ
ክርስቶስ ምሳሌ።
፲፰ ᵐ ሉቃ. ፳፪፡፴፣
፪ ኔፊ ፪፡፲፯–፲፰፤
ት. እና ቃ. ፲፡ ፳፪–፳፯።
፳ ᵐ ማቴ. ፳፭፡፳፪፤
ሐሌ. ፲፡ ፭፤
ሞሮኒ ፯፡ ፳፯፤
ት. እና ቃ. ፹፰፡ ፳፫–፳፭።
፳፩ ᵐ አልማ ፴፡፡ ፳፭።

፳ቮ ነገር ግን ለእነርሱ ᵐፀልዩላቸውና፣ አታባርሩአቸው፤ እናም ዘወትር ወደ እና ንተ የሚመጡ ከሆነ ወደ አብም በስሜ ፀል ዩላቸው።

፳፱ ስለዚህ፣ ለዓለም ያበራ ዘንድ ᵐብርሃ ናችሁን ከፍ አድርጉ። እነሆ፣ እኔ ሳደርግ የተመለከታችሁትም፣ እናንተ ከፍ የምታ ደርጉት ᵃብርሃን ነኝ። እነሆ ወደ አብ መፀ ለዬን ተመልክታችኋል፣ እናም ሁላችሁም መስክራችኋል።

፳፰ እናም ᵐማናችሁም ከዚህ እንዳትርቁ ማዘዜን ተገንዝባችኋል፤ ነገር ግን ᵃትዳስ ሱና ትመለከቱ ዘንድ ወደ እኔ እንድትመጡ አዝዣችኋለሁ፤ በዚሁም ሁኔታ ለዓለም አድርጉ፤ እናም ይህንን ትዕዛዝ የሚያፈ ርስ ቢኖር ወደ ፈተናው ለመግባት ለራሱ ፈቅዷል።

፳፯ እናም እንግዲህ እንዲህ ሆነ ኢየሱስ እነዚህን ቃላት በተናገረ ጊዜ፣ በድጋሚ ወደመረጣቸው ደቀ መዛሙርት ዐይኑን አደረገ፣ እናም እንዲህ ሲል ተናገራቸው፥

፳፯ እነሆ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ሌላ ትዕዛዝ እሰጣችኋለሁ፣ እናም አብም የሰጠኝን ᵐሌሎች ትዕዛዛትን እፈፅም ዘንድ ወደ ᵃአባቴ መሄድ ይገባኛልና።

፳፰ እናም እንዲህ ሆነ እነሆ፣ ለእናንተ የምሰጣችሁ ትዕዛዝ ይህ ነው፤ ቅዱስ ቁርባን በምታቀርቡበት ጊዜ ለማንም ስጋና ደሜን ᵐያለብቁነት ᵃእንዲወስድ አትፍቀዱ፤

፳፱ ᵐያለብቁነት ስጋዬን የሚበላ እናም ᵃደሜን የሚጠጣ ለነፍሱ እርግማንን ይበ ላልና ይጠጣል፤ ስለዚህ አንድ ሰውም ስጋዬን እንደሚበላና ደሜን እንደሚጠጣ ብቁ እንዳልሆነ ካወቃችሁ ከልክሉት።

፴ ይሁን እንጂ፣ ከመካከላችሁ ᵐአታስወ ጡት፣ ነገር ግን እርሱን አገልግሉትና በስሜ ወደ አብ ፀልዩለት፤ እናም በስሜ ንሰሃ ከገ ባና ከተጠመቀ ተቀበሉት እናም ስጋዬንና ደሜን አቅርቡለት።

፴፩ ነገር ግን ንሰሃ ካልገባ፣ ህዝቦቼን እን ዳያጠፋ፣ ከህዝቦቼ መካከል አይቆጠርም፣ እነሆ ᵐበጎቼን አውቃቸዋለሁ፣ እናም እነር ሱም ተቆጥረዋል።

፴፪ ይሁን እንጂ፣ ከምኩራባችሁም ሆነ ከማምለኪያ ስፍራዎቻችሁ አታስወጡ፣ ምክንያቱም ለእነዚህ አይነት ለማገልገል መቀጠል አለባችሁ፤ ምክንያቱም አንድ ቀን እንደሚለወጡና ንሰሃ እንደሚገቡ እናም በልባቸው ሙሉ አላማ ወደ እኔ እን ደሚመጡ አታውቁምና፣ እናም ᵐእፈውሳ ቸዋለሁ፤ እናንተም ይህንነትን ወደ እነርሱ ለማምጣት መሳሪያ ትሆናላችሁ።

፴፫ ስለዚህ ወደ ᵐፍርድ እንዳትመጡ እነ ዚህን ያዘዝኳችሁን ቃላት ጠብቁአቸው፤ አብ ለሚፈርድበት ለዚያ ሰው ወዮለት።

፴፬ እናም በመካከላችሁ በነበረው ፀብ ምክንያት እነዚህን ትዕዛዛት እሰጣችኋ ለሁ። እናም በመካከላችሁ ᵐፀብ ከሌለ እና ንተ የተባረካችሁ ናችሁ።

፴፭ እናም አሁን ᵐለእናንተ ስልም ወደ አብ መሄዴ አስፈላጊ በመሆኑ ወደ አብ እሄ ዳለሁ።

፴፮ እናም እንዲህ ሆነ ኢየሱስ ይህንን ንግግሩን በጨረሰ ጊዜ፣ የመረጣቸውን ᵐደቀመዛሙርት ሁሉንም እስከሚነካ ድረስ አንድ በአንድ ᵃበእጁ ነካቸውና፣ እንደነካ ቸውም ተናገራቸው።

፴፯ እናም ህዝቡም የተናገረውን ቃላት

፳ቮ ሀ ቮ ኔፊ ፲፰፡ ፴።
፳፩ ሀ ማቴ. ፭፡ ፲፮።
ለ ሞዛያ ፲፮፡ ፱።
፳፭ ሀ አልማ ፭፡ ፴ቮ።
ለ ቮ ኔፊ ፲፭፡ ፲፬–፲፮።
፳፮ ሀ ቮ ኔፊ ፲፮፡ ፭–ቮ።
ለ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ—እግዚአብሔር አብ።
፳፯ ሀ ሞር. ፱፡ ፳፱።
ለ ፮ ቆሮ. ፲፭፡ ፳፯–፴።
፳፱ ሀ ት. እና ቃ. ፵፮፡ ፀ።
ለ ቅ.መ.መ. ቅዱስ ቁርባን፤ ደም።
፴ ሀ ት. እና ቃ. ፵፮፡ ቮ።
፴፭ ሀ ዮሐ. ፲፡ ፲ፀ፤ አልማ ፭፡ ፴፰፣ ቮ ኔፊ ፲፭፡ ፳ፀ።
፴፮ ሀ ቮ ኔፊ ፱፡ ፲ቮ–፲ፀ፤ ት. እና ቃ. ፲ፀ፡ ፲ቮ።
፴ቮ ሀ ቅ.መ.መ. መኮነን፣ ኩነኔ።
፴ፀ ሀ ቮ ኔፊ ፲፭፡ ፳፰–፴።
፴፭ ሀ ፭ ዮሐ. ፪፡ ፭፣ ፪ ኔፊ ፪፡ ፱፣ ሞሮኒ ፯፡ ፳፯–፳፰፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡ ፭።
፴፯ ሀ ፭ ኔፊ ፲፪፡ ፯፣ ቮ ኔፊ ፲፱፡ ፱።
ለ ቅ.መ.መ. እጅን መጫን።

አልሰሙትም፤ ስለዚህ አልመሰከሩም፤
ነገር ግን ደቀ መዛሙርቱ [ሀ]መንፈስ ቅዱስን
እንዲሰጡ [ለ]ስልጣንን እንደሰጣቸው መሰ
ከሩ። እናም ከዚህ ጊዜ በኋላም ይህ ምስ
ክርነት እውነት መሆኑንም አሳያችኋለሁ።
፴፰ እናም እንዲህ ሆነ ኢየሱስ ሁሉንም
በነካቸው ጊዜ፣ [ሀ]ደመና መጣና ህዝቡን ሸፈ
ነው ስለዚህ ኢየሱስን ለማየት አልቻሉም።
፴፱ እናም በተሸፈኑ ጊዜ ኢየሱስ ከእነርሱ
ሔደና፣ ወደ ሰማይ አረገ። እናም ደቀመዛ
ሙርቱ ተመለከቱትና በድጋሚ ወደ ሰማይ
ማረጉንም መሰከሩ።

ምዕራፍ ፲፱

አስራ ሁለቱ ደቀመዛሙርት ህዝቡን አስ ተማሩና መንፈስ ቅዱስንም እንዲቀበሉ ፀለዩ—ደቀመዛሙርቱም ተጠመቁና መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ እናም የመላዕክት አገልግሎትንም ተቀበሉ—ኢየሱስ ሊፃፉ የማይችሉ ቃላትን በመጠቀም ፀለየ—ስለነዚህ የኔፋውያንንም እጅግ ታላቅ የሆነ እምነት መሰከረ። ፴፬ ዓ.ም. ገደማ።

፩ እናም እንግዲህ እንዲህ ሆነ ኢየሱስ
ወደ ሰማይ ባረገ ጊዜ፣ ህዝቡ ተበታተነና፣
እያንዳንዱም ሰው ሚስቱንና ልጆቹን በመ
ያዝ ወደ ቤቱ ተመለሰ።
፪ እናም ህዝቡም ኢየሱስን እንደተመለ
ከቱትና እርሱ እንዳስተማራቸው፣ እናም
ደግሞ በሚቀጥለው ቀን እራሱን እንደሚ
ያሳይ ከምሽቱ በፊት ወሬው በህዝቡ መካ
ከል ተዳረሰ።
፫ አዎን፣ እናም ኢየሱስን በተመለከተ
በምሽት ሁሉ ወሬው በፍጥነት ተዳረሰ፤
አዎን፣ በሚቀጥለውም ቀን ኢየሱስ እራ
ሱን ለህዝቡ በሚያሳይበት ስፍራ ይሆኑ
ዘንድ እጅግ ብዙ ቁጥር ወዳላቸው ሰዎች
ተልኮ ምሽቱን ሁሉ ተግተው ሰሩ።
፬ እናም እንዲህ ሆነ በሚቀጥለውም ቀን፣
ህዝቡ በተሰበሰበ ጊዜ፤ እነሆ፣ ኔፊና ከሞት
ያስነሳው ወንድሙ ስሙም ጢሞቴዎስ የተ
ባለውና፣ ደግሞ ዮናስ ተብሎ የሚጠራው
ልጁ፣ እናም ደግሞ ማቶኒና፣ ወንድሙ
ማቶኒያህ፣ እናም ቁመንና፣ ቁመኖንሒ፣
ኤርሚያስም፣ ሼምኖንም፣ ዮናስም፣ ሴዴ
ቅያስም፣ እናም ኢሳይያስ—እንግዲህ እነ
ዚህም ኢየሱስ የመረጣቸው የደቀመዛሙ
ርቱ ስሞች ነበሩ—እናም እንዲህ ሆነ እነ
ርሱ ወደ ፊት ሄዱና በህዝቡ መካከል ቆሙ።
፭ እናም እነሆ፣ ህዝቡም በጣም ብዙ ነበር
ስለዚህ በአስራ ሁለት ቡድን ቦታ እንዲከ
ፈሉ አደረጉ።
፮ እናም አስራ ሁለቱም ህዝቡን አስተ
ማሩ፤ እናም እነሆ፣ ህዝቡም በጉልበቱ
ወደታች ምድር ገፅ ላይ እንዲንበረከኩና፣
በኢየሱስ ስም ወደ አብ እንዲፀልዩ አደረጉ።
፯ እናም ደቀመዛሙርቱም እንዲሁ በኢ
የሱስ ስም ወደ አብ ፀለዩ። እናም እንዲህ
ሆነ ተነሱና ህዝቡን አስተማሩ።
፰ እናም ኢየሱስ የተናገራቸውን ቃላት
ባስተማሩ ጊዜ—ቃላቶቹ ኢየሱስ ከተናገራ
ቸው የተለዩ አልነበሩም—እነሆ፣ በድጋሚ
ተንበረከኩና በኢየሱስ ስም ወደ አብ ፀለዩ።
፱ እናም ይበልጥ ስለሚፈልጉትም ፀለዩ፤
እናም [ሀ]መንፈስ ቅዱስ እንዲሰጣቸው ይፈ
ልጉ ነበር።
፲ እናም እንደዚህ በሚፀልዩም ጊዜ ወደ
ውኃው ጠርዝ ወረዱና ብዙ ህዝብም ተከ
ተላቸው።
፲፩ እናም እንዲህ ሆነ ኔፊ [ሀ]ወደ ውኃው
ወረደና ተጠመቀ።
፲፪ እናም ከውኃው ወጣና ማጥመቅ
ጀመረ። እናም ኢየሱስ የመረጣቸውን
በሙሉ አጠመቃቸው።
፲፫ እናም እንዲህ ሆነ ሁሉም [ሀ]በተጠመ
ቁና ከውኃ በወጡ ጊዜ፣ [ለ]መንፈስ ቅዱስ

፴፯ [ሀ] ቅ.መ.መ. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ።
[ለ] ቅ.መ.መ. ሀይል።
፴፰ [ሀ] ዘፀአ. ፲፱፥፱፣ ፲፮።

፲፱ ፱[ሀ] ፫ ኔፊ ፱፥፳።
፲፩[ሀ] ፫ ኔፊ ፲፩፥፳፫።
፲፫[ሀ] ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣ መጥመቅ።
[ለ] ፫ ኔፊ ፲፪፥፪፤ ሞር. ፯፥፲። ቅ.መ.መ. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ።

በላያቸው ላይ ወረደ፣ እናም በመንፈስ
ቅዱስና በእሳት ተሞልተው ነበር።
፲፡ እናም እነሆ፣ በእሳት ᵐእንደተከበቡ
ያህል ሆነው ነበር፤ እናም እርሱም ከሰማይ
ወረደና ህዝቡም ይህንን ተመልክቷል፣
ምስክርነታቸውንም ሰጡ፤ እናም መላዕ
ክት ከሰማይ ወረዱና አስተማሩአቸው።
፲፩ እናም እንዲህ ሆነ መላዕክት ለደቀ
መዛሙርቱ በሚያስተምሩአቸው ጊዜ፣
እነሆ፣ ኢየሱስ መጣ እናም በመካከላቸው
ቆመና፣ አስተማራቸው።
፲፪ እናም እንዲህ ሆነ ህዝቡንም ተናገ
ረና፣ በድጋሚም በመሬት ላይ እንዲንበረ
ከኩ፣ እናም ደግሞ ደቀመዛሙርቱም በመ
ሬት ላይ እንዲንበረከኩ አዘዛቸው።
፲፫ እናም እንዲህ ሆነ ሁሉም በመሬት
ላይ በተንበረከኩም ጊዜ፣ ደቀመዛሙር
ቱም እንዲፀልዩ አዘዛቸው።
፲፬ እናም እነሆ፣ መጸለይ ጀመሩ፤ እናም
እርሱን ጌታቸውና አምላካቸው በማለት
በመጥራት ወደ ኢየሱስ ፀለዩ።
፲፭ እናም እንዲህ ሆነ ኢየሱስም ከመካከ
ላቸው ወጥቶ ተለይቶአቸው ሄደና፣ ከእነ
ርሱ ትንሽ ራቅ ብሎ ተራመደ፣ እናም ወደ
መሬት አጎነበሰና፣ እንዲህ አለ፥
፲፮ አባት ሆይ፣ እኔ ለመረጥኳቸው ለነዚህ
መንፈስ ቅዱስ ስለሰጠሃቸው አመሰግንሃ
ለሁ፤ እናም በእኔም ባላቸው እምነት ምክ
ንያት ነው ከዓለም የመረጥኳቸው።
፲፯ አባት ሆይ፣ በቃላቸው ለሚያምኑት
ሁሉ መንፈስ ቅዱስህን ትሰጣቸው ዘንድ
እፀልያለሁ።
፲፰ አባት ሆይ፣ በእኔም ስለሚያምኑ መን
ፈስ ቅዱስ ሰጥተሃቸዋል፤ እናም ሰምተሃ
ቸዋልና በእኔም እንደሚያምኑ ተመልክተ
ሃል፣ እነርሱም ወደ እኔም ፀልየዋል፤ እናም
ከእነርሱም ጋር በመሆኔ ወደ እኔ ፀልየዋል።
፲፱ እናም እንግዲህ አባት ሆይ፣ ስለ
እነርሱና ደግሞ በእነርሱ ቃል ለሚያምኑ
ሁሉ በእኔ ያምኑ ዘንድ፣ አብ ሆይ፣ ᵐአንተ
በእኔ እንዳለህ፣ እኔም በእነርሱ እሆን ዘንድ
እኛም ᶠአንድ እንሆን ዘንድ፣ ስለእነርሱ
እፀልያለሁ።
፳፡ እናም እንዲህ ሆነ ኢየሱስ ወደ አብ
በፀለየ ጊዜ፣ ወደ ደቀመዛሙርቱ መጣ፣
እናም እነሆ፣ ወደ እርሱ መፀለያቸውን
አሁንም ሳያቋርጡ ይቀጥሉ ነበር፤ ምን
ᵐመፀለይ እንዳለባቸው ስለተገለፀላቸ
ውም በፀሎታቸው ᶠብዙ ቃላት አይናገ
ሩም ነበር፣ በፍላጎትም ተሞልተው ነበር።
፳፡ እናም እንዲህ ሆነ ኢየሱስ ወደ
እርሱ በሚፀልዩበት ጊዜ ባረካቸው፤ የፊ
ቱም ፈገግታ በላያቸው ላይ ነበር፣ ᵐየፊቱም
ብርሃን ያንፀባርቅባቸው ነበር፣ እናም እነሆ
እነርሱም እንደገፅታውና ደግሞ እንደ ኢየ
ሱስ መጎናፀፊያ ᶠነጭ ነበሩ፤ እናም እነሆ
ንጣታቸውም ከነጭ ነገር ሁሉ እጅግ የበ
ለጠ ነበር፤ አዎን፣ በምድር ላይም በዚያ
ከነበረው ንጣት የበለጠ ሊሆን አይቻለ
ውም ነበር።
፳፪ እናም ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፥
ፀልዩ፤ ይሁን እንጂ ፀሎታቸውን አላቋ
ረጡም ነበር።
፳፫ እናም በድጋሚ ከእነርሱ ተመለሰ፤
ጥቂትም ራቅ ብሎ ሄደና በመሬትም ላይ
አጎነበሰ፤ እናም እንዲህ ሲል በድጋሚ ወደ
አብ ፀለየ፥
፳፬ አባት ሆይ፣ የመረጥኳቸውን በእ
ምነታቸው የተነሳ ᵐስላነፃሃቸው አመሰግ
ንሃለሁ፣ ለእነርሱ እናም ደግሞ በቃላቸው
ለሚያምኑ በቃላታቸው እምነት በእኔ እን
ደተነጹም፣ በእኔ እንዲነጹ ዘንድ ለእነርሱ
እፀልያለሁ።
፳፭ አባት ሆይ፣ በእምነታቸው የተነሳ
በእኔ ይነጹ ዘንድ፤ አብ ሆይ፣ አንተ በእኔ
እንዳለህ እኔና አንተም አንድ እንደሆንን፣

፲፡ ᵐ ሉሊ. ፭፡፳፫–፳፭፣ ፴፫–፴፭፤
፫ ኔፊ ፲፯፡፳፡።
፳፫ ᵐ ፫ ኔፊ ፱፡፲፫።
ᶠ ዮሐ. ፲፯፡፳፩–፳፫።
ቅ.መ.መ. አንድነት።

፳፡ ᵐ ት. እና ቃ. ፴፯፡፴።
ᶠ ማቴ. ፮፡፯።
፳፩ ᵐ ዘኁል. ፮፡፳፫–፳፯።
ᶠ ቅ.መ.መ. መለወጥ—
የተለወጡ ሰዎች።

፳፭ ᵐ ሞሮኒ ፯፡፴፤
ት. እና ቃ. ፶፡፳፳–፳፱፤
፲፫፡፲–፲፬፡፳፭–፳፱።
ቅ.መ.መ. ንጹህነት፣ ንጹህነት።

እኔም በእነርሱ እሆን ዘንድ፤ በእነርሱም
እከብር ዘንድ ስለዓለም ሳይሆን፣ [ሀ]ከአለም
ስለሰጠኸኝ ነው የምጸልየው።
፴ እናም ኢየሱስ እነዚህን ቃላት በተናገረ
ጊዜ በድጋሚ ወደ ደቀመዛሙርቱ መጣ፤
እናም እነሆ ያለማቋረጥ በፅናት ወደ እርሱ
ፀለዩ፤ እርሱም በእነርሱ ላይ ፈገግ አለባ
ቸው፤ እናም እነሆ እነርሱ እንደ ኢየሱስ
[ሁ]ነጭ ነበሩ።
፴፩ እናም እንዲህ ሆነ ትንሽ ራቅ በሎ
ሄደና፣ ወደ አብም ፀለየ፤
፴፪ እናም በፀሎቱ የነበሩትን ቃላት አን
ደበት ሊናገራቸው፣ ወይም የጸለያቸውን
ቃላት ሰው [ሀ]ሊፅፈው አይቻለውም።
፴፫ እናም ህዝቡ አዳመጡና መሰከሩ፤
እናም ልባቸውም ተከፈተና የፀሎቱን ቃላት
በልባቸው ተረዱት።
፴፬ ይሁን እንጂ፣ የፀሎቱ ቃላትም እጅግ
ታላቅና አስገራሚ ስለነበሩ በሰው ሊፃፉም
ሆነ [ሀ]ሊነገሩ አይችሉም።
፴፭ እናም እንዲህ ሆነ ኢየሱስም ፀሎ
ቱን በጨረሰ ጊዜ በድጋሚ ወደ ደቀመዛ
ሙርቱ መጣ፣ እናም እንዲህ አላቸው፤
በአይሁዶች ሁሉ መካከል እንደዚህ ያለ
ታላቅ [ሀ]እምነት በጭራሽ አላየሁም፤ ስለ
ሆነም [ለ]ስለማያምኑ እንደዚህ የሆነ ታላቅ
ተአምራት ላሳያቸው አልቻልኩም።
፴፮ እውነት እላችኋለሁ፣ እናንተ እን
ዳያችሁት እንደዚህ ታላቅ ነገሮችን የተ
መለከተ ከእነርሱ ማንም የለም፤ እንደሰ
ማችሁት ታላቅ ነገሮችንም እነርሱ አልሰ
ሙም ነበር።

ምዕራፍ ፴

*ኢየሱስ በተአምራት ዳቦና ወይኑን አቀ
ረበ፣ እናም በድጋሚ ለህዝቡ ቅዱስ ቁር
ባንን ሰጣቸው—የያዕቆብ ቅሪት የሆኑትም
ጌታ አምላካቸውን ወደማወቁ ይመጣሉና
አሜሪካንም ይወርሳሉ—ኢየሱስ እንደ
ሙሴ ዓይነት ነቢይ ነው፣ እናም ኔፋው
ያን የነቢያቱ ልጆች ናቸው—ሌሎቹ የጌታ
የሆኑት ህዝቦችም በኢየሩሳሌም ይሰበሰ
ባሉ። ፴፩ ዓ. ም. ገደማ።*

፩ እናም እንዲህ ሆነ ህዝቡን እንዲሁም
ደቀመዛሙርቱን [ሀ]ፀሎታቸውን እንዲያ
ቆሙ አዘዛቸው። እናም በልባቸው መፀ
ለይም እንዳያቆሙ አዘዛቸው።
፪ እናም እንዲነሱና በእግራቸው እንዲ
ቆሙ አዘዛቸው። እናም ተነሱና በእግራ
ቸው ቆሙ።
፫ እናም እንዲህ ሆነ በድጋሚ ዳቦውን
ቆረሰውና ባረከው፣ እናም ደቀመዛሙርቱ
እንዲበሉት ሰጣቸው።
፬ እናም በተመገቡም ጊዜ ዳቦውን እን
ዲቆርሱና፣ ለህዝቡ እንዲሰጡ አዘዛቸው።
፭ እናም ዳቦውን ለህዝቡ በሰጡ ጊዜ እርሱ
ደግሞ ወይኑን እንዲጠጡ ሰጣቸው፣ እናም
ለህዝቡ እንዲሰጡም አዘዛቸው።
፮ አሁን፣ በደቀመዛሙርቱም ይሁን በህ
ዝቡ የመጣ ምንም [ሀ]ዳቦም ሆነ ወይን አል
ነበረም።
፯ ነገር ግን እርሱ በእውነት ዳቦ እንዲ
በሉ፣ እናም ደግሞ ወይን እንዲጠጡ [ሀ]ሰጣ
ቸው።
፰ እናም እንዲህ አላቸው፥ ይህንን ዳቦ
[ሀ]የተመገበ ለነፍሱ ስጋዬን ይመገባል፣ ይህ
ንን ወይን የጠጣም ለነፍሱ ደሜን ይጠ
ጣል፤ እናም ነፍሱ አትራብም እንዲሁም
አትጠማም፣ ነገር ግን ትጠግባለች።
፱ እንግዲህ፣ ህዝቡም በሙሉ በተመገቡና
በጠጡ ጊዜ፣ እነሆ፣ በመንፈስ ተሞሉ፤
በአንድም ድምፅ ጮሁ፤ እናም ላዩትና ለሰ
ሙት ኢየሱስ ክብርን ሰጡ።
፲ እናም እንዲህ ሆነ ሁሉም ለኢየሱስ

፴፬ ፩ ሀ ዮሐ. ፲፯፡፲፯።
፴ ፩ ሀ ማቴ. ፲፯፡፪።
፴፪ ፩ ሀ ት. እና ቃ. ፫፯፡፲፲፯።
፴፫ ፩ ፪ ቆሮ. ፲፪፡፩፣
ቮ ኔፊ ፲፯፡፲፯።
፴፭ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
ለ ማቴ. ፲፫፡፶፰።
ቅ.መ.መ. አለማመን።
፴ ፩ ሀ ፪ ኔፊ ፴፪፡፱፣
ሞዛያ ፳፬፡፲፪።
፮ ፩ ሀ ማቴ. ፲፴፡፲፱–፳፭።
፯ ፩ ሀ ዮሐ. ፮፡፱–፲፡።
፰ ፩ ሀ ዮሐ. ፮፡፶–፶፰፣
ቮ ኔፊ ፲፰፡፯።
ቅ.መ.መ. ቅዱስ ቁርባን።

ክብርን በሰጡ ጊዜ፣ እንዲህ አላቸው፥ እነሆ አሁን የእስራኤል ቤት ቅሪት ስለሆኑት ስለነዚህ ሰዎች አብ ያዘዘኝን ትዕዛዝ እፈፅማለሁ።

፲፭ እናም [ሀ]የኢሳይያስም [ለ]ትንቢት ይፈፀማሉ ብዬ የተናገርኳቸሁን አስታውሱ— እነሆ እነርሱ ተፅፈዋል፤ እነርሱም ከፊታችሁ ናቸው፤ ስለዚህ መርምሩዋቸው—

፲፮ እናም የእስራኤል ቤት ሆይ፣ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ እነርሱም ሲፈፀሙ አብም ለህዝቡ የገባው [ሀ]ቃል ኪዳን ይፈፀማል።

፲፯ እናም [ሀ]ቅሪቶቹ፣ በምድር ገፅ ላይ [ለ]የተበተኑት ሁሉ ከምስራቅ፣ ከምዕራብና፣ ከደቡብ፣ እና ከሰሜን [ሐ]ይሰበሰባሉ፤ እናም አዳኛቸው ወደሆነው ወደ ጌታ አምላካቸው [መ]እውቀት ይመጣሉ።

፲፰ እናም አብም ለርስታችሁ ይህችን [ሀ]ምድር እንድሰጣችሁ አዘኛል።

፲፱ እናም እንዲህ እላችኋለሁ፣ አህዛብ በረከቱን በሚቀበሉበት ሁኔታ ህዝቤንም ከበተኑ በኋላ [ሀ]ንሰሃ ካልገቡ—

፲፯ ከዚያም እናንተ የያዕቆብ ቤት ቅሪት የሆናችሁ ከእነርሱም መካከል ትሄዳላችሁ፤ ብዙ ከሚሆኑትም መካከል ትሆናላችሁ፤ እናም [ሀ]አንበሳ ከዱር አውሬዎች መካከል እንደሚሆነውና፣ በመካከላቸው ሲሄድ [ለ]እንደሚረጋግጣቸውና እንደሚቆራርጣቸው፣ እናም ማንም ሊያድናቸው እንደ ማይቻለው እንደ አንበሳ ገልግል በበጎች መንጋ መካከል እንደሚሆን እናንተም በእነርሱ መካከል ትሆናላችሁ።

፲፯ እጅህ በጠላቶችህ ላይ ከፍ ይላል፣ እናም ጠላቶችህ ሁሉ ይጠፋሉ።

፲፰ እናም ሰው አውድማውን በሜዳው ላይ እንደሚሰበስብ ህዝቤን በአንድነት [ሀ]እሰበስባለሁ።

፲፱ አብ ቃል ኪዳን የገባላቸውን ህዝቦቼን፣ አዎን፣ [ሀ]ቀንድሽን ብረት፥ ጥፍርሽንም ናስ አደርጋለሁ። ብዙ ህዝቦችን ታደቅቂአለሽ፤ ትርፋቸውንም ለጌታ፣ ሀብታቸውንም ለምድር ሁሉ ጌታ እቀድሳለሁ። እናም እነሆ፣ ይህን የማደርገውም እኔ ነኝ።

፳ እናም እንዲህ ሆነ፣ አብ እንዲህ አለ፣ በዚያ ቀን የፍርዴ [ሀ]ጎራዴ በእነርሱ ይመዘዛል፤ እናም አብም ንሰሃ ካልገቡ በእነርሱ ላይ ይወድቃል ይላል፤ አዎን፣ በአህዛብ ሀገር ሁሉ ላይም ይወድቃል።

፳፩ እናም እንዲህ ይሆናል የእስራኤል ቤት ሆይ፣ [ሀ]ህዝቤንም እመሰርታለሁ።

፳፪ እናም እነሆ፣ ከአባታችሁ ከያዕቆብ ጋር የገባሁትን [ሀ]ቃል ኪዳን እፈፅም ዘንድ ይህን ህዝብ በዚህች ምድር እመሰርታለሁ፤ እርሷም [ለ]አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ትሆናለች። እናም የሰማይ ስልጣናትም በዚህ ህዝብ መካከል ይሆናሉ፤ አዎን፣ [ሐ]እኔም በመካከላችሁ እሆናለሁ።

፳፫ እነሆ፣ ሙሴ እንዲህ ሲል የተናገረለት እኔ ነኝ፥ ከወንድሞቻችሁ እንደ እኔ ያለን [ሀ]ነቢይ ጌታ አምላካችሁ ከመካከላችሁ ያስነሳል፤ እርሱ የሚላችሁን ሁሉ ታደምጡታላችሁ። እናም ይህን ነቢይ የማትሰማ ነፍስ ብትኖር ከዚህ ህዝብ ተለይታ ትጠፋለች።

፲፭ ሀ ፪ ኔፊ ፳፭፡፩–፭፤ ሞር. ፯፡፳፫።
ለ ፫ ኔፊ ፲፮፡፲፯–፳፡ ፳፫፡፩–፫።
፲፮ ሀ ፫ ኔፊ ፲፫፡፯–፡፡
፲፯ ሀ ፫ ኔፊ ፲፮፡፲፩–፲፭፤ ፳፩፡፲፪–፳፡
ለ ቅ.መ.መ. እስራኤል— የተበተኑት እስራኤል።
ሐ ቅ.መ.መ. እስራኤል— የእስራኤል መሰብሰብ።
መ ፫ ኔፊ ፲፮፡፱–፳።
፲፱ ሀ ቅ.መ.መ. የቃል ኪዳን ምድር።
፲፭ ሀ ፫ ኔፊ ፲፮፡፣–፲፱።
፲፯ ሀ ሞር. ፭፡፳፱፤ ት. እና ቃ. ፲፱፡፳፯።
ለ ሚክ. ፭፡፰–፱፤ ፫ ኔፊ ፲፮፡፲፩–፲፭፤ ፳፩፡፲፪።
፲፰ ሀ ሚክ. ፱፡፲፪።
፲፱ ሀ ሚክ. ፱፡፲፣።
፳ ሀ ፫ ኔፊ ፳፲፡፱።
፳፩ ሀ ፫ ኔፊ ፲፮፡፰–፲፭።
፳፪ ሀ ዘፍጥ. ፶፱፡፳፪–፳፯፤ ት. እና ቃ. ፶፯፡፪–፫።
ለ ኢሳ. ፪፡፪–፭፤ ፫ ኔፊ ፳፩፡፳፣–፳፡፤ ኤተር ፲፣፡፩–፲፪፤ ት. እና ቃ. ፲፡፱–፡፡ ቅ.መ.መ. አዲሲቱ ኢየሩሳሌም።
ሐ ኢሳ. ፶፱፡፳–፳፩፤ ሚል. ፣፡፩፤ ፫ ኔፊ ፳፡፩።
፳፣ ሀ ዘዳግ. ፲፰፡፲፭–፲፱፤ የሐዋ. ፣፡፳፪–፳፣፤ ፩ ኔፊ ፳፪፡፳–፳፩።

፳፪ እውነት እላችኋለሁ፤ አዎን፣ እናም ከሳሙኤል ጀምሮ ከእርሱ በኋላ የተናገሩት ᵐነቢያት ሁሉ ስለእኔ መስክረዋል።

፳፫ እናም እነሆ፣ እናንተ የነቢያት ልጆች ናችሁ፤ እናም የእስራኤል ቤት ናችሁና፣ እግዚአብሔር ለአብርሃም በዘርህ የምድር ᵐወገኖች ሁሉ ይባረካሉ ብሎ ከአባቶቻችሁ ጋር ያደረገው ᵃየኪዳን ልጆች ናችሁ፤

፳፬ አብም ወደእናንተ በመጀመሪያ እን ድነሳ አደረገኝ፣ እናም ከክፋቶቹ እያንዳ ንዳችሁን ᵐእንዳርቅ እናንተን እንድባርክ ላከኝ፤ እናም ይህም የሆነው እናንተ የቃል ኪዳን ልጆች ስለሆናችሁ ነው—

፳፭ እናም ከተባረካችሁ በኋላ እንዲህም ሲል አብ ከአብርሃም ጋር የገባው ቃል ኪዳን ተፈፅሟል፥ በዘርህ የምድር ᵐወገኖች በሙሉ ይባረካሉ—በእኔም በኩል ወደ አህ ዛብ መንፈስ ቅዱስን ወደማፍሰስ፣ ይህም ᵃበአህዛብ ላይ ያለው በረከት ከሁሉም በላይ ሀይለኛ ሆነው ህዝቤን፣ አቤቱ የእስራኤል ቤትን፣ ይበትናሉ።

፳፮ እናም ለዚህች ምድር ህዝቦች ᵐጅራፍ ይሆናሉ። ይሁን እንጂ፣ አብም የወንጌሌን ሙሉነት በሚቀበሉበት ጊዜ ልባቸውን በእኔም ላይ ካጠጡሩ፣ ክፋታ ቸውን በእራሳቸው ላይ እመልስባቸዋለሁ ይላል።

፳፱ እናም ከህዝቤ ጋር የገባሁትን ቃል ኪዳን ᵐአስታውሳለሁ፤ አብም እንዲህ ይላል፥ በራሴም ጊዜ በአንድ ላይ እነር ሱን ᵃእንድሰበስብ፤ ለዘሮቻቸውም በድ ጋሚ ᶜየኢየሩሳሌምን ምድር የሆነውን፣ እናም ለዘለዓለም የቃል ኪዳን ምድር የሆ ነችላቸውን የአባቶቻቸውን ᵐምድር ለመ ስጠት ቃል ኪዳን ገብቻለሁና።

፴ እናም የወንጌሌ ሙሉነት ለእነርሱ የሚሰበክበት ጊዜ ይመጣል፤

፴፩ እናም እኔም የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆንኩኝ በእኔ ᵐያም ናሉ፣ እናም በስሜም ወደ አብ ይፀልያሉ።

፴፪ ᵐጠባቂዎቻቸውም ድምፃቸውን ከፍ ያደርጋሉ፣ እናም በአንድ ድምፅም ይዘም ራሉ፤ ዐይን ለዐይንም ይተያያሉና።

፴፫ ከዚያም አብ በድጋሚ በአንድነት ይሰበስባቸዋል፣ እናም ለርስታቸውም ምድር ኢየሩሳሌምን ይሰጣቸዋል።

፴፬ እነርሱም እልል ይላሉ—እናንተ የተ በላሻችሁ የኢየሩሳሌም ስፍራዎች በአንድ ነት ᵐዘምሩ፤ አብም ህዝቡን አፅናንቷል፤ ኢየሩሳሌንም አድኗልና።

፴፭ አብም ቅዱስ የሆኑ ክንዶቹን በሀገር ሁሉ ፊት አሳይቷል፤ እናም በዓለም ጫፍ ያሉት ሁሉ የአብን መድሀኒት ይመለከ ታሉ፤ እናም እኔና አብም አንድ ነን።

፴፮ እና ከዚያም የተፃፉትም ይፈፀማሉ፤ ፅዮን ሆይ ᵐንቂ፣ በድጋሚ ንቂና፣ ጥንካ ሬሽን ልበሺ፤ ኢየሩሳሌም ሆይ፣ ቅዲሲቷ ከተማ ሆይ፣ ያጌጠ ልብስሽንም ልበሺ፤ ከእንግዲህ ያልተገረዘና ርኩስ ወዳንቺ ዘንድ አይመጣምና።

፴፯ ኢየሩሳሌም ሆይ ትቢያሽን አራግፊ፣ ተነሺ፣ ተቀመጪ፤ ምርኮኛይቱ የፅዮን ልጅ ሆይ የአንገትሽን እስራት ፍቺ።

፴፰ ጌታ እንዲህ ይላልና፥ በከንቱ ተሽጣችሁ ነበር፤ ያለገንዘብም ትቤዣላ ችሁ።

፴፱ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ህዝቤ ስሜን ያውቃሉ፤ አዎን በዚያ ቀን የምናገ ረው እኔ እንደሆንኩም ያውቃሉ።

፵ እናም ከዚያም እንዲህ ይላሉ፥ ሰላምን

፳፩ ᴴ የሐዋ. ፫ ፡ ፳፬–፳፮፤
፩ ኔፊ ፲ ፡ ፭፤
ያዕቆ. ፯ ፡ ፲፩።
፳፭ ᴴ ዘፍጥ. ፲፪ ፡ ፩–፫፤ ፳፪ ፡ ፲፰።
ለ ቅ.መ.መ. የአብርሐም ቃል ኪዳን።
፳፮ ᴴ ምሳ. ፲፯ ፡ ፮።
፳፯ ᴴ ገላ. ፫ ፡ ፳፤
፪ ኔፊ ፳፱ ፡ ፲፬፤
አብር. ፪ ፡ ፱።
ለ ፫ ኔፊ ፲፯ ፡ ፮–፯።
፳፰ ᴴ ፫ ኔፊ ፲፯ ፡ ፳–፱።
፳፱ ᴴ ኢሳ. ፶፪ ፡ ፳፩፤
፫ ኔፊ ፲፯ ፡ ፲፩–፲፪።
ለ ቅ.መ.መ. እስራኤል—የእስራኤል መሰብሰብ።
ሐ ቅ.መ.መ. ኢየሩሳሌም።
መ ዓሞ. ፱ ፡ ፲፬–፲፭።
፴፩ ᴴ ፫ ኔፊ ፳ ፡ ፳፩–፳፯፤
፳፩ ፡ ፳፯–፳፱።
፴፪ ᴴ ኢሳ. ፶፪ ፡ ፰፤
፫ ኔፊ ፲፯ ፡ ፲፰–፲፡
ት. እና ቃ. ፱፲፫ ፡ ፯–፲።
ቅ.መ.መ. ፅዮን።

ᵐያበስር፤ ᵃመልካም የሆነውን መልካም የምስራች ወሬ ያመጣ፣ ደህንነትን ያወጀ፣ ለፅዮንም አምላካችሁ ነግሶአል! ያለው፣ መልካም የምስራች ይዞ የመጣው በተራራው ላይ ያለው እግሮቹ እንዴት ያማሩ ናቸው።

፶፮ እናም እንዲህ የሚልም ጩኸት ይሆ ናል፡ ᵐሽሹ፣ ᵐሽሹ፣ ከዚህ ስፍራ ᵃተለዩ፣ ርኩስ የሆነውንም አትንኩ፤ ከመካከልዋም ውጡ፤ የጌታን ዕቃ የምትሸከሙ ᵃንፁሃን ሁኑ።

፶፯ በችኮላም ሆነ በመሸሽ ᵐአትሄዱም፤ ጌታ ከፊታችሁ ይሄዳልና፣ እናም የእስራ ኤል አምላክም ከኋላችሁ ይሆናል።

፶፰ እነሆ አገልጋዬ በማስተዋል ያደር ጋል፤ ይከበራል እናም ከፍ ከፍም ይላል፤ እጅግ ታላቅም ይሆናል።

፶፱ ብዙዎች በአንተ ተደንቀው ነበር— ፊቱም ከማንኛውም ሰው የበለጠ፣ እናም የሰውነቱም ገጽ ከሰው ልጆች የበለጠ የተ በላሸ ነበር—

፷ በብዙ ሀገርም ላይ ᵐያርከፈክፋል፤ ያልተነገረላቸውንም ያያሉና፡ ያልሰሙ ትንም ያስተውላሉና፣ ነገሥታት ስለ እርሱ አፋቸውን ይዘጋሉ።

፷፩ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ አብ እንዳዘዘኝ እነዚህ ነገሮች ሁሉ በእርግጥ ይመ ጣሉ። አብም ከህዝቡ ጋር የገባው ይህ ቃል ኪዳን ይፈፀማል፤ እናም ህዝቦቼም በድጋሚ ᵐኢየሩሳሌምን ይኖሩባታል፤ እናም እርሷም የርስት ምድራቸው ትሆናለች።

ምዕራፍ ፳፩

መፅሐፈ ሞርሞን ሲመጣ እስራኤል ትሰበ ሰባለች—አህዛብም ነፃ ህዝብ በመሆን በአ ሜሪካ ይደራጃሉ—ካመኑ እናም ታዛዥ ከሆኑ ይድናሉ፤ አለበለዚያ ይቆረጣሉ እናም ይጠፋሉ—እስራኤል አዲሲቷን ኢየሩሳሌ ትመሰርታለች፣ እናም የጠፉት ነገዶችም ይመለሳሉ። ፴፬ ዓ.ም. ገደማ።

፩ እናም እውነት እላችኋለሁ፣ እነዚህ ነገ ሮች፣ ህዝቤን የእስራኤልን ቤት፣ ለረጅም ጊዜ ከተበተኑበት የምሰበስበት፣ እናም በድጋሚም ፅዮንንም በመካከላቸው የም መሰርትበት የሚፈፀሙበትን ᵐጊዜ ታውቁ ዘንድ ምልክትን እሰጣችኋለሁ—

፪ እናም እነሆ፣ ለምልክት እንዲሆናችሁ የምሰጣችሁ ነገር ይህ ነው—እውነት እላች ኋለሁ የያዕቆብ ቤት ስለሆኑት እነዚህ ሰዎች በተመለከተ፣ እናም በእነርሱም ስለሚበተ ኑት ህዝቦቼ በተመለከተ እነዚህን የምነግ ራችሁና፣ ከዚህ በኋላም በራሴና፣ አብም በሚሰጣችሁ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካ ኝነት የሚታወጅላችሁ ነገሮች ያውቁ ዘንድ ለአህዛብ እንዲያውቁት ይደረጋል፤

፫ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ በአብ አማካኝነት ᵐእነዚህን ነገሮች እንዲያውቁ በሚደረግበት እናም በአብም ከእነርሱም ወደ እናንተ በሚመጣበት ጊዜ፤

፬ እነዚህ ነገሮች ከእነርሱ ለዘራችሁ ቅሪት ይመጡ ዘንድ፤ ይኸውም አብ ከህዝቡ ከእ ስራኤል ቤት ጋር የገባው ᵐቃል ኪዳን ይፈ ፀም ዘንድ፣ ይህ እነርሱ በዚች ምድር ይደ ራጁ ዘንድ፣ እናም በአብ ኃይልም ᵃነፃ ሰዎች በመሆን ይቋቋሙ ዘንድ፣ ይህ የአብ ጥበብ ነውና።

፭ ስለዚህ፣ ይህም ሥራ እናም በመካ ከላቸሁ ከዚህም በኋላ የሚሰራው ᵐበአህ ዛብ አማካኝነት በክፋታቸው እምነት አጥ

፯ *ሀ* ማር. ፲፫፡፲፣
፭ ኔፊ ፲፫፡ ፴፯።
ለ ኢሳ. ፶፪፡ ፯፣
ናሆ ፩፡ ፲፭፤
ሞዛያ ፲፭፡ ፲፫–፲፰፤
ት.እና ቃ. ፲፳፰፡ ፲፱።
፯፩ *ሀ* ኢሳ. ፶፪፡ ፲፩–፲፫።
ለ ቅ.መ.መ. ንጹህ እና ርኩስ።

ሐ ት.እና ቃ. ፲፴፫፡ ፭።
፯፪ *ሀ* ፲ ኔፊ ፳፩፡ ፳፱።
፯፭ *ሀ* ኢሳ. ፶፪፡ ፲፭።
፯፮ *ሀ* ኤተር ፲፫፡ ፭፣ ፲፭።
፳፩ ፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. የመጨረሻ ቀናት፣ የኋለኛው ቀናት።
፲ *ሀ* ኤተር ፪፡ ፲፯፤
ጆ.ስ.—ታ. ፩፡ ፴፪–፴፮።

፪ *ሀ* ሞር. ፭፡ ፳።
ቅ.መ.መ. የአብርሐም ቃል ኪዳን።
ለ ፩ ኔፊ ፲፫፡ ፲፯–፲፱፤
ት.እና ቃ. ፲፩፡ ፳፯–፳፱።
፭ *ሀ* ፲ ኔፊ ፳፯፮፡ ፳።

ተው ለመነመኑት ^ለዘሮቻችሁ በሚደር ስበት ጊዜ፤

፮ ኃይሉን ለአህዛብ ያሳይ ዘንድ፣ ይህም ᵛከአህዛብ እንዲመጣ፣ ይኸውም አህዛብ ልባቸውን ካላጠጡሩ፣ ንሰሃ ቢገቡና በስሜ ቢጠመቁ እናም የትምህርቴን እውነተኛ ነጥቦች ቢያውቁ፤ ከህዝቦቼም ከእስራኤል ቤት ጋር ^እንዲቆጠሩ የአብ ፈቃድ ነውና፤

፯ እናም እነዚህ ነገሮች በሚሆኑበት ጊዜ ᵛዘሮቻችሁ እነዚህን ነገሮች ማወቅ ይጀምራሉ—ይህም የእስራኤል ቤት ለሆኑት የገባው ቃል ኪዳን እንዲፈፀም የአብ ስራ እንደተጀመረ እንዲያውቁ ዘንድ ለምልክት ይሆንላቸዋል።

፰ እናም ያ ቀን በሚመጣበትም ጊዜም ነገሥታት አፋቸውን ይዘጋሉ፤ ያልተነገራቸውን ያያሉና፤ እናም ያልሰሙትን ያስተውላሉን።

፱ በዚያን ቀን፣ ለእኔም ሲል አብ ሥራን ይሰራል፣ ሥራውም በመካከላቸው ታላቅ እንዲሁም ᵛድንቅ ሥራ ይሆናል፤ እናም አንድ ሰው ለእነርሱ ቢያውጅላቸውም በእነርሱ መካከል ይህን የማያምኑ ይኖራሉ።

፲ ነገር ግን እነሆ፣ የአገልጋዬ ህይወት በእጄ ትሆናለች፤ ስለዚህ ምንም እንኳን በእነርሱ የተነሳ እርሱ ᵛቢጠፋም፣ አይጎዱትም። ይሁን እንጂ እርሱን እፈውሰዋለሁ፤ ^ማስተዋሌም ከዲያብሎስ ሴራ የበለጠ መሆኑን አሳያቸዋለሁ።

፲፩ ስለዚህ አብም ᵛእርሱን ወደ አህዛብ እንዲያመጣው ባደረገው፣ እናም ለአህዛብ ያመጣው ዘንድ ስልጣንን በሰጠው ኢየሱስ ክርስቶስ በሆንኩት በእኔ ቃል የማያምን፣ (ሙሴ እንደተናገረውም ይፈፀማል) የቃል ኪዳን ህዝብ ከሆኑት ከህዝቦቼም መካከል ^ይለያል።

፲፪ እናም ህዝቤ የያዕቆብ ቅሪት የሆኑት ከአህዛብ መካከል ይሆናሉ፤ አዎን በመካከላቸው በዱር አውሬዎች መካከል እንዳለ ᵛአንበሳ፣ በበጎች መንጋ መካከል ከሄደ ^እንደሚረጋግጣቸውና፣ እንደሚቆራጣቸው የአንበሳ ግልገል ይሆናሉ፣ እናም ማንም ለማዳን አይቻለውም።

፲፫ እጃቸው በጠላቶቻቸው ላይ ከፍ ይላል፣ እናም ጠላቶቻቸው ሁሉ ይጠፋሉ።

፲፬ አዎን፣ ᵛንሰሃ ካልገቡ ለአህዛብ ወዮላቸው፤ አብም እንዲህ ይሆናል ይላል፣ በዚያም ቀን ፈረሶቼን ከመካከላቸው አጠፋለሁ፣ ሰረገሎቻቸውንም እሰብራለሁ።

፲፭ እናም የምድራችሁን ከተሞች አጠፋለሁና ምሽጎቻችሁን በሙሉ አፈራርሳለሁ፤

፲፮ እናም መተትንም ከምድራችሁ አጠፋለሁና፣ ምዋርተኞችም ከእንግዲህ አይኖራችሁም፤

፲፯ ᵛየተቀረፀውን ምስላችሁን እና ሐውልቶቻችሁንም ደግሞ በመካከላችሁ አጠፋለሁ፣ እናም ከእንግዲህ የእጆቻችሁን ስራ አታመልኩም፤

፲፰ እናም የማምለኪያ ዐፀዶቻችህንም ከመካከላችሁ እነቅላለሁ፥ ከተማዎቻችሁንም አፈርሳለሁ።

፲፱ እናም እንዲህ ይሆናል፣ ᵛሀሰቶችም፣ ማጭበርበርም፣ ምቀኝነትም፣ ፀብም፣ የካህናት ተንኮል፣ እናም ዝሙት ሁሉ ከእንግዲህ ይወገዳሉ።

፳ አብም እንዲህም ይሆናልና ይላል፣ የእስራኤል ቤት ሆይ፣ በዚያን ቀን ንሰሃ

፭ *ለ* ፪ ኔፊ ፴፡፱–፭፤
ሞር. ፭፡፲፭፤
ት. እና ቃ. ፫፡፲፰–፲፱።
፮ *ሀ* ፩ ኔፊ ፲፡፲፬፤
ያዕቆ. ፭፡፶፬፤
፫ ኔፊ ፲፮፡፱–፮።
ለ ገላ. ፫፡፮፣ ፳፱፤
፫ ኔፊ ፲፮፡፲፫፤
አብር. ፪፡፱–፲፩።
፯ *ሀ* ፫ ኔፊ ፭፡፳፩–፳፯።

፱ *ሀ* ኢሳ. ፳፱፡፲፬፤
የሐዋ. ፲፫፡፶፩፤
፩ ኔፊ ፳፪፡፳።
ቅ.መ.መ. የወንጌል ዳግም መመለስ።
፲ *ሀ* ት. እና ቃ. ፻ሀ፳፭፡፩–፫።
ለ ት. እና ቃ. ፲፡፶፫።
፲፩ *ሀ* ፪ ኔፊ ፫፡፮–፲፭፤
ሞር. ፳፡፲፯፣ ፳፭።
ለ ት. እና ቃ. ፩፡፲፬።

፲፪ *ሀ* ሚክ. ፭፡፳–፲፭፤
፫ ኔፊ ፳፡፲፯።
ለ ፫ ኔፊ ፲፯፡፲፣ ፲፡፲–፲፭።
፲፬ *ሀ* ፪ ኔፊ ፲፡፲፣ ፴፫፡፱።
፲፯ *ሀ* ዘፀአ. ፳፡፫–፴፤
ሞዛያ ፲፫፡፲፪–፲፫፤
ት. እና ቃ. ፩፡፲፯።
ቅ.መ.መ. ጣአት አምላኪ።
፲፱ *ሀ* ፫ ኔፊ ፴፡፪።

ያልገባ፣ እናም ወደ ተወደደው ልጄ ያል
መጣ ከህዝቤ መካከል እለየዋለሁ፤
፳፩ እናም አረመኔዎች ላይ እንደማደርገ
ውም፣ በእነርሱም ላይ ተለማምደው በማ
ያውቁት ዓይነት ቁጣ እና መዓት እበቀላ
ቸዋለሁ።
፳፪ ነገር ግን ንሰሃ ከገቡና ቃሌን ካዳ
መጡ፣ እናም ልባቸውንም ካላጠጠሩ፣
ቤተክርስቲያኔን በእነርሱ መካከል ሀእመ
ሰርታለሁና፣ ወደ ቃልኪዳኑ ይመጣሉ፣
እናም ለርስታቸውም ምድሪቷን ከሰጠኋ
ቸው ከእነዚህ ከያዕቆብ ቅሪቶች ጋር ለይቆ
ጠራሉ።
፳፫ እናም የያዕቆብ ቅሪት የሆኑ ህዝቦቼ
ንና፣ ደግሞ የሚመጡትን የእስራኤል ቤት
የሆኑትን ሁሉ፣ እነርሱም ሀአዲሲቷ ኢየሩ
ሳሌም ተብላ የምትጠራውን ከተማ ይመሰ
ርቱ ዘንድ ይረዳሉ።
፳፬ እናም ከዚያም በምድረ ገፅ ላይ
በሙሉ የተበተኑትን፣ በአዲሲቷ ኢየሩ
ሳሌም ይሰባሰቡ ዘንድ ህዝቦቼን ይረዳሉ።
፳፭ እና ከዚያም ሀየሰማይ ኃይልም በእ
ነርሱ መካከል ይወርዳል፤ እናም ደግሞ
ለእኔም በመካከላቸው እሆናለሁ።
፳፮ እናም በዚያን ቀንም ይህም ወንጌል
በዚህ ህዝብ ቅሪት በሆኑት መካከል በሚ
ሰበክበት ወቅት የአብ ስራ ሀይጀመራል።
እውነት እላችኋለሁ፣ በዚያን ቀን በተበ
ተኑት ህዝቦቼ መካከል፣ አዎን፣ አብ ከኢ
የሩሳሌም ባስወጣቸው፣ ለበጠፉት ነገዶ
ችም መካከል ቢሆን የአብ ስራ ይጀመራል።
፳፯ አዎን፣ አብን በስሜ ይጠሩት ዘንድ
ወደ እኔም እንዲመጡ መንገዱን ለማዘ
ጋጀት ሀበተበተኑት ህዝቦቼ ሁሉ መካከል
ስራው ከአብ ጋር ይጀመራል።
፳፰ አዎን፣ እናም ህዝቡም ወደ ራሱ
ሀገር፣ ወደ ርስት ምድሩ ሀይሰበሰብ ዘንድ
መንገድን በማዘጋጀት በሀገሪቱ ሁሉ መካ
ከል ከአብ ጋር ስራው ይጀመራል።
፳፱ እናም እነርሱም ከሁሉም ሀገሮች
ይወጣሉ፤ እናም ሀበችኮላም ሆነ በመኮብ
ለል አይሄዱም፣ አብም እኔም በፊታቸው
እሄዳለሁም፣ በኋላቸውም ጠባቂአቸው
እሆናለሁ ይላልና።

ምዕራፍ ፳፪

*በመጨረሻው ቀን ፅዮንና ካስሚያዎ
ችዋ ይቋቋማሉ፣ እናም እስራኤል በም
ህረትና በደግነት ይሰበሰባሉ—እነርሱም
አሸናፊ ይሆናሉ—ኢሳይያስ ፶፬ን አነ
ጻፅሩ። ፴፬ ዓ.ም. ገደማ።*

፩ እናም የተፃፈውም እንዲህ ይፈፀማል፥
አንቺ ያልወለድሽ መካን ሆይ ዘምሪ፤ አንቺ
ያላማጥሽ እልል በይ፤ እናም ሀበዝማሬ
ጩኺ፣ ባል ካላት ይልቅ ፈት የሆነችው
ልጆች በዝተዋልና ይላል ጌታ።
፪ የድንኳንሽን ስፍራ አስፊ፤ መጋረጃዎ
ችሽንም ይዘርጉ፤ አትቆጥቢ፣ ገመድሽን
አስረዝሚና ሀካስሞችሽንም አፅኚ፤
፫ በቀኝና በግራም ትስፋፊያለሽ፣ እናም
ዘሮችሽም ሀአህዛብን ይወርሳሉና የፈረሱ
ትን ከተሞች መኖሪያ ያደርጋሉ።
፬ አታፍሪምና አትፍሪ፤ እንድታፍሪ
ስለማይደረግ ዝም አትበይ፤ የልጅነትሽን
ሀእፍረት ትረሺዋለሽ፣ የልጅነትሽን ብሉሽ
ነትሽን ውቅት ከእንግዲህ አታስታውሺም፣
የመበለትነትሽንም ወቅት ከእንግዲህ ወዲህ
አታስቢውም።
፭ ፈጣሪሽ ባልሽ ነው፤ ስሙም የሰራዊት

፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. ዘመን።
ለ ፪ ኔፊ ፲፥፲፰–፲፱፤
፫ ኔፊ ፲፮፥፲፫።
፳፫ ሀ ፫ ኔፊ ፳፥፳፪፤
ኤተር ፲፫፥፩–፲፪።
ቅ.መ.መ. አዲሲቱ
ኢየሩሳሌም።
፳፭ ሀ ፩ ኔፊ ፲፫፥፴፯።
ለ ኢሳ. ፪፥፪–፬፤
፫ ኔፊ ፳፬፥፩።
፳፮ ሀ ፩ ኔፊ ፲፬፥፲፯፤
፫ ኔፊ ፳፩፥፮–፯።
ለ ቅ.መ.መ. እስራኤል—
የጠፉት የእስራኤል አስር
ነሳዎች።
፳፯ ሀ ፫ ኔፊ ፲፮፥፬–፭።
፳፰ ሀ ቅ.መ.መ. እስራኤል—
የእስራኤል መሰብሰብ።
፳፱ ሀ ኢሳ. ፶፪፥፲፪፤
፫ ኔፊ ፳፥፵፪።
፳፪ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. መዘመር።
፪ ሀ ቅ.መ.መ. ካስማ።
፫ ሀ ቅ.መ.መ. አህዛቦች።
፬ ሀ ፪ ኔፊ ፮፥፯፣ ፲፫።

ጌታ ነው፤ እናም የእስራኤል ቅዱስ የሆነ ውም አዳኝሽ ነው—የምድር ሁሉ አምላክ ተብሎም ይጠራል።

፮ ጌታ እንደተተወችና እንደተበሳጨች መንፈስ፣ እናም በልጅነት እንደጣሉአት ሚስት ጠርቶሻል ይላል አምላክሽ።

፯ ለጥቂት ጊዜ ጣልኩሽ፣ ነገር ግን በታ ላቅ ምህረት እሰበስብሻለሁ።

፰ በጥቂት ቁጣ ለቅፅበት ፊቴን ከአንቺ ሰወርኩ፣ ነገር ግን በዘለዓለም ቸርነት "እም ርሻለሁ ይላል ጌታ አዳኝሽ።

፱ "ይህ ለእኔ እንደ ^ኖህ ውኃ ነው፤ የኖህ ውሃ ደግሞ በምድር ላይ እንዳያልፍ እንደ ማልሁ እንዲሁ አንቺን እንዳልቆጣ እንዳ ልዘልፍሽም ምያለሁ።

፲ "ተራሮች ይፈርሳሉ፤ ኮረብቶችም ይወ ገዳሉ፣ ቸርነቴ ግን ከአንቺ ዘንድ ^አያል ፍም፣ የሰላሜም ቃል ኪዳን አይወገድም ይላል መሃሪሽ የሆነ ጌታ።

፲፩ አንቺ የተቸገርሽ ሆይ፣ በአውሎ ነፋ ስም የተናወጥሽ፣ ያልተፅናናሽም! እነሆ፣ "ድንጋዮችሽን ሸላልሜ እገነባለሁ፤ በሰ ንፔርም ጌጥ እመሰርትሻለሁ።

፲፪ የግንብሽንም ጉልላት በቀይ ዕንቁ፤ በሮችሽንም በሚያብረቀርቅ ዕንቁ፤ ዳርቻሽንም ሁሉ በከበሩ ድንጋዮች እሰ ራለሁ።

፲፫ እናም "ልጆችሽ ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ፤ እናም የልጆችሽም ሰላም ታላቅ ይሆናል።

፲፬ "በፅድቅ ትታነፂያለሽ፤ ከግፍ አድራጊ አትፈሪምና ድንጋጤም ወደ አንቺ አይቀ ርብም።

፲፭ እነሆ፣ በእርግጥም ባንቺ ላይ ይሰበሰ ባሉ ነገር ግን ከእኔ ዘንድ አይሆንም፤ በአ ንቺም ላይ የሚሰበሰቡ ሁሉ ከአንቺ የተነሳ ይወድቃሉ።

፲፮ እነሆ፣ ፍሙን በወናፍ የሚያናፋ ለስ ራውም መሳሪያ የሚያወጣ ብር ሰሪን እኔ ፈጥሬአለሁ።

፲፯ በአንቺ ላይ የተሰራ መሳሪያ ሁሉ አይ ከናወንም፣ በፍርድም በሚነሳብሽ ምላስ ሁሉ ትፈርጂበታለሽ። የጌታ ባሪያዎች ቅርስ ይህ ነው፤ ጽድቃቸውም ከእኔ ዘንድ ነው ይላል ጌታ።

ምዕራፍ ፳፲

ኢየሱስ የኢሳይያስን ቃላት አጸ ደቀ—ህዝቡ ነቢያትን እንዲፈልጉ አዘዘ—ላማናዊው ሳሙኤል ስለትንሣኤ የተናገራቸው ቃላት በመዝገቦቻቸው ተጨምረዋል። ፴፬ ዓ.ም. ገደማ።

፩ እናም እንግዲህ፣ እነሆ፣ እንዲህ እላ ችኋለሁ፣ እነዚህን ነገሮች "ፈልጉ። አዎን፣ እነዚህን ነገሮች በትጋት እንድትፈልጉ ትዕዛዝ እሰጣችኋለሁ፤ ^የኢሳይያስ ቃላት ታላቅ ናቸውና።

፪ የእስራኤል ቤት የሆኑትን ህዝቦቼን በተ መለከተ፣ ስለሁሉም ነገሮች በእርግጥ ተና ግሯል፤ ስለዚህ ለአህዛብ ደግሞ መናገሩ አስፈላጊ ነው።

፫ እናም የተናገራቸው፣ እንዲሁም በተ ናገራቸው ቃላት መሰረት፣ ሁሉም ነገሮች ሆነዋልም፣ "ይሆናሉም።

፬ ስለዚህ ቃሌን ልብ ብላችሁ አድምጡ፤ የተናገርኳችሁንም ነገሮች ፃፉ፤ እናም በአብ ጊዜና ፈቃድ መሰረት እነርሱ ወደ አህዛብ ይሄዳሉ።

፭ እናም ቃሌን የሚሰማና ንሰሃ የሚገባ እናም የሚጠመቅ እርሱ ይድናል። "ነቢያ ትን ፈልጓቸው፣ ስለነዚህ ነገሮች የሚመ ሰክሩ ብዙዎች በዚያ ናቸውና።

፮ እናም እንዲህ ሆነ ኢየሱስ እነዚህን

፳ *ሀ* ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።
፱ *ሀ* ኢሳ. ፶፬፡፱።
ለ ቅ.መ.መ. የኖኅ ዘመን የጥፋት ውሀ።
፲ *ሀ* ኢሳ. ፵፡፬።
ለ መዝ. ፻፴፡፲፤ ት.እና ቃ. ፴፭፡፳፭።
፲፩ *ሀ* ራዕ. ፳፩፡፲፳–፳፩።
፲፫ *ሀ* ኤር. ፴፩፡፴፣–፴፬።
፲፬ *ሀ* ቅ.መ.መ. ጻድቅ፣ ጽድቅ።
፳፲ ፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. ቅዱሳት መጻህፍት።
ለ ፪ ኔፊ ፳፭፡፩–፭፣ ሞር. ፳፡፳፲። ቅ.መ.መ. ኢሳይያስ።
፲ *ሀ* ፲ ኔፊ ፳፡፲፤–፲፪።
፭ *ሀ* ሉቃ. ፳፬፡፣ ፳፭–፳፯።

ቃላት በድጋሚ በተናገራቸው ጊዜ፣ የተ
ቀበሉአቸውን ቅዱሳን መፃህፍት በጥል
ቀት ካስረዳቸው በኋላ እንዲህ ሲል ተና
ገራቸው፥ እነሆ፣ እናንተ ያልጻፍኳቸው፣
እንድትፅፉ የፈለግሁት ሌሎች ቅዱሳን
መጽሐፍት አሉ።

፣ እናም እንዲህ ሆነ ለኔፊም እንዲህ
አለው፥ ያስቀመጥከውን መዝገብ አምጣ።

፤ እናም ኔፊም መዛግብቱን ባመጣና
ከፊቱ ባደረገውም ጊዜ፣ ኢየሱስ ተመለ
ከታቸውና እንዲህ አለ፥

፥ እውነት እላችኋለሁ፣ አገልጋዬን
ላማናዊውን ᵐሳሙኤል በዛን ቀን አብ በእኔ
ስሙን በሚያስከብርበት ጊዜ ᵃብዙ የሞቱ
ᵃᵃቅዱሳን ᵐእንደሚነሱና ለብዙዎች እን
ደሚታዩ፣ እናም እነርሱንም እንደሚያ
ስተምሩ ለዚህ ህዝብ እንዲመሰክር አዘዝ
ኩት። እናም ይህ አልነበረምን? ብሎ ተና
ገራቸው።

፦ እናም ደቀመዛሙርቱ እንዲህ ሲሉ
መለሱለት፥ አዎን፣ ጌታ ሆይ፣ ሳሙኤል
በቃልህ መሰረት ተንብዮ ነበር፣ እናም
ሁሉም ተፈጽመው ነበር።

፲፩ እናም ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፥ ብዙ
ዎች ቅዱሳን እንደተነሱና፣ ለብዙዎች እን
ደተገለጡና እነርሱን እንዳስተማሩ እንዴት
አልተፃፉም?

፲፪ እናም እንዲህ ሆነ ኔፊም ይህ ነገር እን
ዳልተፃፈ አስታወሰ።

፲፫ እናም እንዲህ ሆነ ኢየሱስም መፃፍ
እንዳለበት አዘዘ፤ ስለዚህ እርሱ እንዳዘዘ
ውም ተፃፈ።

፲፬ እናም እንዲህ ሆነ ኢየሱስም እነርሱ
የፃፉትን ቅዱሳን መጽሐፍትን በሙሉ በአ
ንድ ላይ ᵐበአስረዳቸው ጊዜ፣ እርሱም ለእ
ነርሱ ያስረዳቸውን ነገሮች ማስተማር እን
ዳለባቸው አዘዛቸው።

ምዕራፍ ፳፩

*የጌታ መልዕክተኛ የክርስቶን ዳግም ምፅ
ዓት መንገድ ያዘጋጃል—ክርስቶስ በፍርድ
ወንበር ይቀመጣል—እስራኤል አስራትን
እናም በኩራትን እንዲከፍል ታዛለች—
የመታሰቢያ መጽሐፍ ተጠብቋል—
ሚልክያስ ᵐን አነጻፅሩ። ፴፩ ዓ.ም. ገደማ።*

፩ እናም እንዲህ ሆነ የሚነግራቸውን፣
አብም ለሚልኪያስ የሰጠውን ቃላት እን
ዲጽፉት አዘዛቸው። እናም እንዲህ ሆነ ከጻ
ፉትም በኋላ አስረዳቸው። እናም እንዲህ
በማለት ለእነርሱም የነገራቸው ቃላት እነ
ዚህ ናቸው፥ አብም ለሚልኪያስ እንዲህ
ሲል ተናገረው—እነሆ፣ ᵐመልዕክተኛዬን
እልከዋለሁ፣ እርሱም መንገዱን ከፊቴ ያዘ
ጋጃል፣ እናም የምትፈልጉት ጌታም በድን
ገት ወደ መቅደሱ ይመጣል፤ ያውም የም
ትወዱት የቃል ኪዳን መልዕክተኛ፣ እነሆ፣
ይመጣል፣ ይላል የሠራዊት ጌታ።

፪ ነገር ግን የሚመጣበትን ቀን ᵐመታገስ
የሚችልና በተገለጠ ጊዜም የሚቆም ማን
ነው? እርሱ እንደ ᵃአንጥረኛ እሳት እናም
እንደ አጣቢ የሚያጠራ ሳሙና ነውና።

፫ እናም እርሱም ብርን እንደሚያነጥርና
እንደሚያጠራ ሰው ይቀመጣል፤ ᵐየሌዊ
ንም ልጆች ያጠራል፣ እንደ ወርቅና ብርም
ያነጥራቸዋል፣ እነርሱም ለጌታ በፅድቅ
መስዋዕት ᵃየሚያቀርቡ ይሆናሉ።

፬ ጌታም እንደ ድሮው ዘመንና እንደቀ
ደሙት ዓመታት በይሁዳና በኢየሩሳሌም
መስዋዕት ደስ ይለዋል።

፭ እናም ለፍርድ ወደ እናንተ እቀርባ
ለሁ፤ እናም በመተተኞችና፣ በአመንዝ
ሮች፣ በሀሰትም በሚምሉና፣ የምንደኛውን
ደሞዝ በሚከለክሉ፣ እናም መበለቲቱንና
ᵐድሃ አደጉን በሚያስጨንቁ፣ እንዲሁም

፱ ᵐ ሉሌ. ፲፫፡፪።
ᵃ ሉሌ. ፲፬፡ ፳፭።
ᵃᵃ ቅ.መ.መ. ቅዱሳን።
ᵐ ማቴ. ፳፯፡ ፶፪–፶፫።
ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
፲፩ ᵐ ሉቃ. ፳፬፡ ፴፱–፴፯።

፳፩ ፩ ᵐ ት. እና ቃ. ፴፯፡ ፱።
፪ ᵐ ፫ ኔፊ ፳፭፡ ፩።
ᵃ ዘካ. ፲፫፡ ፱፣
ት. እና ቃ. ፻፳፯፡ ፳፩።
ቅ.መ.መ. ምድር—
ምድርን ማፅዳት፣
የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም
ምፅዓት።
፫ ᵐ ዘዳግ. ፲፡ ፳፣
ት. እና ቃ. ፹፱፡ ፴፩–፴፬።
ᵃ ት. እና ቃ. ፲፫፡።
፭ ᵐ ያዕ. ፩፡ ፳፯።

በመጻተኛውም ፍርድን በሚያጣምሙ እኔ ንም በማይፈሩ ላይ ፈጣን ምስክር እሆንባ ቸዋለሁ ይላል የሰራዊት ጌታ።

፮ እኔ ጌታ ነኝና አልለወጥም፤ ስለዚህ እናንተ የያዕቆብ ልጆች የጠፋችሁ አይደ ላችሁም።

፯ ከአባቶቻችሁ ዘመን ጀምሮ ከስርዓቴ [ሀ]ፈቀቅ ብላችኋል፣ እናም አልጠበቃችኋቸ ውም። ወደ እኔ [ለ]ተመለሱና እኔ ወደ እናንተ እመለሳለሁ ይላል የሰራዊት ጌታ። እናንተ ግን የምንመለሰው ወዴት ነው? ብላችኋል።

፰ ሰው እግዚአብሔርን ይሰርቃልን? እና ንተ ግን እኔን ሰርቃችኋል። ነገር ግን እን ዴት ነው አንተን የሰርቅነው? ብላችኋል። [ሀ]በአስራትና [ለ]በበኩራት ነው።

፱ እናንተ፥ ይህ ሀገር ሁሉ እኔን ሰርቋልና በእርግማን ርጉሞች ናችሁ።

፲ በቤቴ ውስጥ መብል እንዲሆን [ሀ]አስራ ቱን ሁሉ ወደ ጎተራው አግቡ፤ የሰማይንም መስኮት ባልከፍትላችሁ [ለ]በረከቴንም አት ረፍርፌ ባላፈስላችሁ በዚህ ፈትኑኝ ይላል የሠራዊት ጌታ።

፲፩ እናም ስለእናንተ ነቀዙን እገስፃለሁ፣ እናም የምድራችሁን ፍሬ አያጠፋም፣ በእ ርሻችሁም ያለው ወይን ፍሬውን አያረ ግፍም ይላል የሠራዊት ጌታ።

፲፪ እናም የተድላ ምድር ትሆናላችሁና፣ ሀገር ሁሉ ብፁዓን ብለው ይጠሩአችኋል ይላል የሠራዊት ጌታ።

፲፫ ቃላችሁ በእኔ ላይ ድፍረት ሆኖአል ይላል ጌታ። እናንተ ግን፣ በአንተ ላይ የተ ናገርነው ምንድነው? ብላችኋል።

፲፬ እናንተ እግዚአብሔርን ማገልገል ከንቱ ነው፣ ስርአቶቹን በመጠበቅ በሠራ ዊት ጌታ ፊት ሃዘንተኞች ሆነን በመራመድ ምን ይረባናል? ብላችኋል።

፲፭ እናም አሁን የሚታበዩትን ሰዎች ብፁዐን ብለው ይጠሩአቸዋል፤ አዎን ክፉ ንም የሚሰሩ ጸንተዋል፤ አዎን እግዚአብ ሔርን የሚፈታተኑ ይለቀቃሉ።

፲፮ ጌታን የሚፈሩ እርስ በርሳቸው ሁል ጊዜ [ሀ]ይነጋገራሉ፤ እናም ጌታ አደመጠ፤ እናም ሰማም፤ ጌታን ለሚፈሩ ስሙንም ለሚያስቡ [ለ]የመታሰቢያ መጽሐፍ በፊቱ ተፃፈ።

፲፯ እናም ጌጤን [ሀ]ስሰራ በዚያን ቀን የእኔ ይሆናሉ ይላል የሠራዊት ጌታ፤ እናም ሰው የሚያገለግለውን ልጁን እንደሚምር እን ዲሁ እምራቸዋለሁ።

፲፰ ተመልሳችሁም በፃድቁና በኃጢአ ተኛው መካከል፣ ለእግዚአብሔር በሚገ ዛውና በማይገዛው መካከል [ሀ]ትለያላችሁ።

ምዕራፍ ፳፭

በዳግም ምፅዓት ጊዜ ትዕቢተኞች፣ እናም ኃጢአተኞች እንደገለባ ይቃጠ ላሉ—ኤልያስ ከታላቁና ከአስፈሪው ቀን በፊት ይመለሳል—ሚልክያስ ፬ን አነ ጻፅሩ። ፴፬ ዓ.ም. ገደማ።

፩ እነሆም፣ እንደ ምድጃ እሳት [ሀ]የሚነድ ቀን ይመጣል፤ እናም [ለ]ትዕቢተኞች ሁሉ አዎን፣ እናም ኃጢያትን የሚሰሩ ሁሉ ገለባ ይሆናሉ፤ የሚመጣውም ቀን ያቃጥ ላቸዋል፤ ሥርንና ቅርንጫፍንም አይተው ላቸውም ይላል የሠራዊት ጌታ።

፪ ነገር ግን ስሜን ለምትፈሩ፣ ለእናንተ [ሀ]የፅድቅም ልጅ ፈውስን በክንፎቹ ይዞ ይነ

፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. ክህደት።
ለ ሐለ. ፲፫፡፲፩፤ ፫ ኔፊ ፲፡፯፤ ሞሮኒ ፱፡፳፪።
፰ *ሀ* ቅ.መ.መ. አስራት፣ አስራት መክፈል።
ለ ቅ.መ.መ. በኩራት።
፲ *ሀ* ት. እና ቃ. ፳፱፡፳፫፣ ፻፲፱።
ለ ቅ.መ.መ. መባረክ፣ የተባረከ፣ በረከት።
፲፯ *ሀ* ሞሮኒ ፮፡፭።
ለ ት. እና ቃ. ፹፫፡፱፣ ሙሴ ፮፡፭። ቅ.መ.መ. የመታሰቢያ መፅሐፍ።
፲፯ *ሀ* ት. እና ቃ. ፻፭፡፫።
፲፰ *ሀ* ቅ.መ.መ. የመለየት ስጦታ።
፳፭ ፩ *ሀ* ኢሳ. ፳፱፡፮፤ ፩ ኔፊ ፳፪፡፲፭፤ ፫ ኔፊ ፳፡፲፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፱፣ ፳፡፲–፳፡፣ ፻፴፫፡፳፡፤ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡ ፴፯። ቅ.መ.መ. ምድር—ምድርን ማፅዳት።
ለ ፪ ኔፊ ፳፡፱፣ ፴፫። ቅ.መ.መ. ኩራት።
፪ *ሀ* ኤተር ፱፡ ፳፪።

ሳል፤ እናንተም ትወጣላችሁ እናም ^እንደ ጥጃም በበረት ሓታድጋላችሁ።

፫ እናም ክፉዎችን ᵛትረግጡአቸዋላችሁ፤ እናም ይህንን በምሰራበት ቀን በደለኞች ከእግራችሁ ሥር አመድ ይሆናሉ፣ ይላል የሠራዊት ጌታ።

፬ ለእስራኤል ሁሉ ስርዓትንና ፍርድን አድርጌ ᵛበኮሬብ ያዘዝሁትን የባሪያዬን የሙሴን ህግ አስቡ።

፭ እነሆ፣ ታላቁና የሚያስፈራው የጌታ ᵛቀን ሳይመጣ ነቢዩ ^ኤልያስን እልክላች ኋለሁ፤

፮ እናም ምድርን በእርግማን እንዳልመታ እርሱ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች፣ የልጆ ችንም ልብ ወደ አባቶች ᵛይመልሳል።

ምዕራፍ ፳፮

ኢየሱስ ከመጀመሪያ እስከመጨረሻው ያሉትን ነገሮች በሙሉ አብራራ—ህፃናት እንዲሁም ልጆች ሊፃፉ የማይችሉ አስደ ናቂ ነገሮችን ተናገሩ—በክርስቶስ ቤተክር ስቲያን የነበሩት በመካከላቸው ሁሉም ነገ ሮች በጋራ ነበሩአቸው። ፴፬ ዓ.ም. ገደማ።

፩ እናም እንግዲህ እንዲህ ሆነ ኢየሱስ እነዚህን ነገሮች በተናገራቸው ጊዜ እነዚ ህን ለህዝቡ አብራራ፤ እናም ትልቅ እንዲ ሁም ትንሽ የሆኑትን ሁሉንም ነገሮች አብ ራራላቸው።

፪ እናም እንዲህ አለ፥ እናንተ የሌላችሁን

ᵛእነዚህ ቅዱሳን መጽሐፍት አብ እንድሰ ጣችሁ አዟል፤ ለመጪው ትውልድ መስ ጠት እንደሚገባቸው የእርሱ ጥበብ ነው።

፫ እናም ከመጀመሪያው ጀምሮ ᵛበክብሩ እስከሚመጣ ድረስ ያሉትን ሁሉንም ነገ ሮች—አዎን፣ በምድር ገፅ ላይ የሚመጡ ትን ነገሮች ሁሉ፣ የምድር ^ማዕድናትም በታላቅ ሙቀት እስከሚቀልጡ ድረስና፣ ምድርም እንደ መጽሐፍ ጥቅልል ^እስ ከምትጠቀለል፣ እናም ሰማይና ምድርም እስከሚያልፉ እንኳን አብራራላቸው፤

፬ እናም ሀገር ሁሉ፣ እናም ነገዶች ሁሉ፣ እናም ሁሉም ህዝቦችና ቋንቋ በሙሉ መል ካም ይሁኑም መጥፎ፣ እንደስራቸው እን ዲፈረድባቸው በእግዚአብሔር ፊት ᵛስለ ሚቆሙበት ^ታላቁና በመጨረሻው ቀንም እንኳን—

፭ መልካም ከሆኑም፣ ለዘለዓለማዊው ህይ ወት ᵛትንሳኤ፤ ክፉ ከሆኑም፣ ወደኩነኔም ትንሳኤ፤ ^ከአለም በፊት በነበረው ክርስ ቶስ ምህረትና፣ ^ሓፍትህ፣ እና ቅድስና መሰ ረት፣ አንደኛው በአንድ እጅ እናም ሌላኛው በሌላ እጅ በመሆን እነዚህ የተገናኙ ናቸው።

፮ እናም እንግዲህ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ኢየሱስ በእውነት ለህዝቡ ካስተማራቸው ነገሮች ᵛአንድ መቶኛው እንኳን ሊፃፍ አል ተቻለም፤

፯ ነገር ግን እነሆ ᵛየኔፊ ሠሌዳዎች ህዝቡን ስላስተማራቸው ነገሮች በይበልጥ ይዘዋል።

፰ እናም እኔ የጻፍኳቸው እነዚህ ነገ

፪ *ለ* ዓሞ. ፯፡፱፤
፩ ኔፊ ፳፪፡፳፬።
ሐ ት. እና ቃ. ፵፭፡፶፰።
፫ *ሀ* ፫ ኔፊ ፳፭፡፲፪።
፬ *ሀ* ዘፀአ. ፫፡፩–፯።
፭ *ሀ* ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
ለ ፪ ነገሥ. ፪፡፩–፪፤
ት. እና ቃ. ፪፡፩፤
ያዕ. ፲፫–፲፮፤
ያዕ.፡ ፲፫–፲፮፤
ቅ.መ.መ. ለሙታን ደህንነት፤
ማተም፣ ማስተሳሰር፤
ኤልያስ።
፯ *ሀ* ት. እና ቃ. ፪፡፪።
፳፯ ፪ *ሀ* ይህም በ፫ ኔፊ ፳፬ እና ፳፭ ውስጥ የተጠቀሰው ሚል. ፫ እና ፬ ማለት ነው።
፫ *ሀ* ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—የክርስቶስ ክብር።
ለ ዓሞ. ፱፡፲፫፤
፪ ጴጥ. ፫፡፲፣ ፲፪፤
ሞር. ፱፡፪።
ቅ.መ.መ. ምድር—ምድርን ማፅዳት፤ አለም—የአለም መጨረሻ።
ሐ ሞር. ፭፡፳፫።
፱ *ሀ* ሞዛያ ፲፯፡፲–፲፩።
ቅ.መ.መ. ፍርድ፣ የመጨረሻው።
ለ ሔለ. ፲፪፡፳፭፤
፫ ኔፊ ፳፰፡፴፤
፭ *ሀ* ዳን. ፲፪፡፪፤
ዮሐ. ፭፡፳፱።
ለ ኤተር ፫፡፲፩።
ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—የክርስቶስ ቅድመ ምድራዊ ህይወት።
ሐ ቅ.መ.መ. ፍትህ።
፮ *ሀ* ዮሐ. ፳፭፡፳፭፤
፫ ኔፊ ፭፡፰።
፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. ሰሌዳዎች።

ሮች፣ እርሱ ካስተማራቸው ነገሮች ጥቂቶች ናቸው፤ እናም እነርሱም ኢየሱስ በተናገ ራቸው ቃላት መሰረት እነዚህ ለዚህ ህዝብ በድጋሚ ᵐከአህዛብ ይመጡ ዘንድ ፅፌአ ቸዋለሁ።

፱ እናም እምነታቸውን በመጀመሪያ እን ዲፈትኑበት ይህን መቀበላቸው አስፈላጊ ስለሆነ፣ ይህን በተቀበሉበት ጊዜ፣ እናም እነዚህን ነገሮች የሚያምኗቸው ከሆነ ከዚ ያም ᵐታላላቅ የሆኑት ነገሮች ይገለፁላቸ ዋል።

፲ እናም እነዚህን ነገሮች የማያምኑ ከሆኑ፣ ታላላቆቹ ነገሮችም እነርሱን ይኮንኑ ዘንድ ᵐአይገለፁላቸውም።

፲፩ እነሆ፣ በኔፊ ሠሌዳዎች ላይ የተፃፉ ትን ሁሉ ለመፃፍ ተዘጋጅቼ ነበር፣ ነገር ግን ጌታ እንዲህ በማለት ከልክሎኛል፥ የህዝ ቤን እምነት ᵐእፈትናለሁ።

፲፪ ስለዚህ እኔ ሞርሞን፣ በጌታ የታዘዝ ኩባቸውን ነገሮች እፅፋለሁ። እናም እን ግዲህ እኔ ሞርሞን ንግግሬን አበቃለሁ፤ እናም የታዘዝኳቸውን ነገሮች መፃፌን እቀ ጥላለሁ።

፲፫ ስለዚህ፣ ጌታም ለሶስት ቀናት በእው ነት ህዝቡን እንዳስተማረ እንድትመለከቱ እፈልጋለሁ፤ እናም ከዚያ በኋላ በተደጋ ጋሚ ራሱን ᵐአሳይቷቸዋል፣ እናም በተደ ጋጋሚም ᵃዳቦ በመቁረስ ባርኮ ሰጥቷቸዋል።

፲፬ እናም እንዲህ ሆነ የተነገረላቸውን ሰዎች ᵐልጆችም ኢየሱስ አስተማራቸውና አገለገላቸው፣ እናም አንደበታቸውን ፈታ ላቸውና፣ ለህዝቡ እርሱ ከገለፀላቸው የበ ለጡትን ለአባቶቻቸው ታላቅና አስገራሚ የሆኑ ነገሮችን ተናገሩ፤ እናም ለመናገር እንዲችሉም አንደበታቸውን ᵃፈታላቸው።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ ወደ ሰማይም ካረገ በኋላ—ለሁለተኛ ጊዜ እራሱን ገለ ፀላቸው፣ እናም በሽተኞቻቸውንና ሽባዎ ችን በሙሉ ᵐከፈወሰና፣ የዕውሮችን ዐይን ካበራ፣ እናም የደንቆሮን ጆሮዎች ከከፈ ተና፣ ሁሉንም ዐይነት ፈውሶች በመካከ ላቸው ካደረገ በኋላ፣ እናም አንድን ሰው ከሞት ካስነሳና ኃይሉንም ካሳያቸው በኋላ ወደአብ ሄደ—

፲፮ እነሆ፣ እንዲህ ሆነ በሚቀጥለው ቀን ህዝቡ በአንድ ላይ ተሰበሰበ፣ እናም እነዚ ህን ልጆች ተመለከቱአቸውና፣ አዳመጡ አቸው፣ አዎን፣ ᵐህፃናቱም አፋቸውን ከፈ ቱና፣ አስደናቂ ነገሮችን ተናገሩ፤ እናም የተናገሩአቸውን ነገሮች ማንም እንዳይፅፍ ተከልክሏል።

፲፯ እናም እንዲህ ሆነ ኢየሱስ የመረጣ ቸው ᵐደቀመዛሙርት ከዚያን ጊዜ በኋላ ወደ እነርሱ የመጡትን ሰዎች ሁሉ ማጥ መቅና ማስተማር ጀመሩ፤ እናም በኢየሱስ ስም ᵃየተጠመቁት ሰዎች በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው ነበር።

፲፰ እናም ብዙዎች ሊፃፉ ᵐበህግ ያልተፈ ቀዱትን፣ ሊነገሩ የማይችሉ ነገሮችን ተመ ልክተዋልም፣ ሰምተዋልም።

፲፱ እናም አንዳቸው ሌላኛውን አገለገ ሉና፣ አስተማሩ፤ እንዲሁም እያንዳንዱ ሰውም እርስ በርሱ በፍትህ በማገልገል፣ በመካከላቸው ᵐሁሉም ነገሮች ᵃበጋራ ነበ ሩአቸው።

፳ እናም እንዲህ ሆነ ኢየሱስ እንዳዘዛቸው ሁሉንም ነገሮች አደረጉ።

፳፩ እናም በኢየሱስ ስም የተጠመቁት ᵐየክርስቶስ ቤተክርስቲያን ተብለው ይጠሩ ነበር።

፳ ᵐ ፫ ኔፊ ፳፩፡፳–፳፤።
፱ ᵐ ኤተር ፬፡፭–፲።
፲ ᵐ አልማ ፲፪፡፱–፲፩።
፲፩ ᵐ ኤተር ፲፪፡፲።
፲፫ ᵐ ዮሐ. ፳፩፡፲፬።
ᵃ ፫ ኔፊ ፳፡፫–፱።
ቅ.መ.መ. ቅዱስ ቁርባን።
፲፬ ᵐ ፫ ኔፊ ፲፯፡፲፩–፲፪።
ᵃ አልማ ፴፪፡፳፫፣
፫ ኔፊ ፳፯፡፲፯።
፲፭ ᵐ ፫ ኔፊ ፲፯፡፱።
ቅ.መ.መ. መፈወስ፣
ፈውሶች፣
ተአምራት።
፲፯ ᵐ ማቴ. ፲፩፡፳፭።
፲፯ ᵐ ፫ ኔፊ ፲፱፡፱–፲፫።
ᵃ ፱ ኔፊ ፩፡፩።
፲፰ ᵐ ፫ ኔፊ ፳፤፡፲፯።
፲፱ ᵐ ፱ ኔፊ ፩፡፩።
ᵃ ቅ.መ.መ. መቀደስ፣ የቅድስና
ህግ።
፳፩ ᵐ ሞዛያ ፲፰፡፲፯።
ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ
ቤተክርስቲያን።

ምዕራፍ ፳፯

ኢየሱስ ቤተክርስቲያኗን በስሙ እንዲጠሩ አዘዛቸው—ወንጌሉም አገልግሎቱንና የኃጢያት ክፍያውን የያዘ ነው—ሰዎች በመንፈስ ቅዱስም ይነፁ ዘንድ ንሰሃ እን ዲገቡና እንዲጠመቁ ታዘዋል—ኢየሱስ እንደሚሆነውም ይሁኑ። ከ፴፬–፴፰ ዓ.ም. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ የኢየሱስ ደቀመዛ ሙርት በተጓዙበት እናም ስለተመለከቱ አቸውና ስለሰሙአቸው ነገሮች በሰበኩበ ትና፣ በኢየሱስ ስም ባጠመቁበት ወቅት፣ እንዲህ ሆነ ደቀመዛሙርቱ [ሀ]በአንድ ላይ ተሰባስበው ነበር፣ እናም በብርቱ ፀሎታ ቸውና [ለ]ያማቸው አንድ ሆነው ነበር።

፪ እናም ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱ ወደ አብ በስሙ በመፀለያቸው በድጋሚ ራሱን [ሀ]አሳ ያቸው፤ እናም ኢየሱስ መጣና በመካከላ ቸው ቆመ፣ እንዲህም አላቸው፥ ምን እን ድሰጣችሁ ትፈልጋላችሁ?

፫ እናም እንዲህ አሉት፥ ጌታ ይህንን ቤተክርስቲያን የምንጠራበትን ስም እንድ ትነግረን እንፈልጋለን፤ ምክንያቱም ይህንን በተመለከተ በህዝቡ መካከል ጥል አለና።

፬ እናም ጌታም እንዲህ አላቸው፥ እው ነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ህዝቡ ስለዚህ ነገር ለምን ያጉረመርማል እንዲሁም ይጣ ላል?

፭ ስሜ የሆነውን፣ [ሀ]የክርስቶስን ስም በእ ራሳቸው ላይ መውሰድ እንዳለባቸው ቅዱ ሳን መጻሕፍትን አላነበቡምን? በዚህ ስም በመጨረሻው ዘመን ትጠሩበታላችሁና፤

፮ እናም ስሜን በራሱ ላይ የወሰደና፣ እስ ከመጨረሻው በዚህ [ሀ]የፀና በመጨረሻው ዘመን እርሱ ይድናል።

፯ ስለዚህ፣ ማንኛውንም ነገር ስታደ ርጉ፣ በስሜ አድርጉት፤ ስለዚህ ቤተክር ስቲያኗን በስሜ ጥሯት፤ እናም ወደ አብም በስሜ ፀልዩ እርሱም ለእኔም ሲል ቤተክ ርስቲያኗን ይባርካታል።

፰ እናም በስሜ ካልተጠራ [ሀ]የእኔ [ለ]ቤተ ክርስቲያን እንዴት ሊሆን ይችላል? ቤተ ክርስቲያኗ በሙሴ ስም ከተጠራች የሙሴ ቤተክርስቲያን ትሆናለች፤ ወይም በሰው ስም ከተጠራች የሰው ቤተክርስቲያን ትሆ ናለች፤ ነገር ግን በወንጌሌ ላይ የተገነቡ ከሆኑ፣ በስሜ ከተጠራች የእኔ ቤተክርስ ቲያን ትሆናለች።

፱ እውነት እላችኋለሁ፣ በወንጌሌ ላይ ታንፃችኋል፤ ስለዚህ የምታደርጉትን ማን ኛውንም ነገር በስሜ ትጠራላችሁ፤ ስለዚህ ለቤተክርስቲያኗ ወደ አብ በስሜ ከፀለያችሁ አብ ይሰማችኋል፤

፲ እናም ቤተክርስቲያኗ በወንጌሌ ላይ ከታነፀች አብም ስራውን ይገልፅባታል።

፲፩ ነገር ግን በወንጌሌ ላይ ካልታነፀች፣ እናም በሰዎች ስራ ላይ፣ ወይም በዲያ ብሎስ ስራ ላይ ከታነፀች፣ እውነት እላ ችኋለሁ ለጊዜው በስራቸው ደስታን ያገ ኛሉ፣ እናም ከጥቂት ጊዜም በኋላ ፍፃሜ አቸው ይመጣልም፣ እናም [ሀ]ይፈረካከሳ ሉም፣ መመለስ በማይቻልበት እሳት ውስ ጥም ይወድቃሉ።

፲፪ ስራቸው [ሀ]ይከተላቸዋልና፣ በስራቸው ምክንያትም ተቆርጠው ወድቀዋልና፤ ስለ ዚህ የነገርኳችሁን ነገሮች አስታውሱ።

፲፫ እነሆ [ሀ]ወንጌሌን ሰጥቻችኋለሁ፣ እናም ለእናንተ የሰጠኋችሁ ወንጌልም ይህ ነው—ወደ ዓለም የመጣሁት የአባቴን [ለ]ፈቃድ ለመፈፀም ነው፣ ምክንያቱም አባቴ ልኮ ኛልና።

፳፯ ፩ *ሀ* ት. እና ቃ. ፳፱፡፮።
ለ አልማ ፮፡፮።
ቅ.መ.መ. ጾም፣ መጾም።
፪ *ሀ* ፫ ኔፊ ፳፯፡፲፫።
ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—ክርስቶስ ከሚችነት በኋላ መገለጡ።
፭ *ሀ* ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—የክርስቶስን ስም በራሳችን ላይ መውሰድ።
፮ *ሀ* ፫ ኔፊ ፲፭፡፱።
፰ *ሀ* ት. እና ቃ. ፸፲፭፡፩።
ለ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—የቤተክርስትያኗ ራስ።
፲፩ *ሀ* አልማ ፭፡፶፪።
፲፪ *ሀ* ራዕ. ፲፬፡፲፣ ት. እና ቃ. ፶፱፡፪።
፲፫ *ሀ* ት. እና ቃ. ፫፯፡፶–፶፪።
ቅ.መ.መ. ወንጌል።
ለ ዮሐ. ፮፡፴፰–፴፱።

፲ዕ አባቴም በመስቀል ᵐእሰቀል ዘንድ ልኮኛል፤ እናም በመስቀል ላይ ከተሰቀ ልኩ በኋላ፣ ሰዎችን ሁሉ ወደ ራሴ ᵃአመጣ ዘንድ፣ እኔ በሰዎች እንደተሰቀልኩ በአብ አማካኝነት ሰዎች ይነሱ ዘንድ፣ መልካምም ይሁኑ መጥፎ በስራቸው ᵃእንዲፈረድባ ቸው በእኔ ፊት ለመቆም ይችሉ ዘንድ፣ ተሰቅያለሁ—

፲፭ እናም ለዚህም ምክንያት ᵐተሰቀል ኩኝ፤ ስለዚህ፣ በአብ ስልጣን መሰረት ሰዎች በሙሉ በስራቸው ይፈረድባቸው ዘንድ ወደ እኔ እንዲመጡ አደረግሁ።

፲፮ እናም እንዲህ ይሆናል ማንኛውም ᵐንሰሃ የገባና በስሜ ᵃየተጠመቀ ይሞላል፤ እናም እስከመጨረሻው ᵃከፀናም እነሆ ዓለ ምን የምፈርድበት ቀን ስትመጣ በአብ ፊት ከበደል የነፃ አደርገዋለሁ።

፲፯ እናም እስከመጨረሻው ፀንቶ የማይ ቀጥል ግን በአብ ᵐፍትህ የተነሳ፣ ተቆርጦ መጨረሻ ወደሌለው፣ ወደእሳቱ የሚጣል እርሱ ነው።

፲፰ እናም ለሰው ልጆች የሰጣት ይህች ቃል ናት። እናም በዚህ የተነሳ የተሰጠውን ቃላት ይፈፅማል፣ እናም አይዋሽም፣ ነገር ግን ቃሉን በሙሉ ይፈፅማል።

፲፱ እናም በመንግስተ ሰማይ ᵐምንም እር ኩስ ነገር ሊገባ አይቻለውም፤ ስለዚህ በእ ምነታቸው እናም ለኃጢአታቸው ሁሉ ንሰሃ በመግባታቸውና እስከመጨረሻው ባላቸው ታማኝነት በደሜ ልብሳቸውን ᵃካጠቡት በስተቀር ᵃበእረፍቱ የሚገባ ማንም የለም።

፳ እንግዲህ ትዕዛዜ ይህች ናት፥ በምድር ዳርቻ ያላችሁ ሁሉ ᵐንሰሃ ግቡ፣ እናም መን ፈስ ቅዱስን በመቀበል ᵃትቀደሱ ዘንድ፤ በመጨረሻው ቀን በፊቴ ᵃያለእንከን ትቆሙ ዘንድ ወደ እኔ ኑ፣ እናም በስሜ ᵐተጠመቁ።

፳፩ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ይህ የእኔ ወንጌል ነው፤ እናም በቤተክርስቲ ያኔም መስራት ያለባችሁንም ነገሮች ታው ቃላችሁና፤ እኔ ስሰራው ያያችሁትን ስራ እናንተም ደግሞ ስሩ፤ ስሰራ ያያችሁትን ስራ እናንተም ያን ታደርጋላችሁ፤

፳፪ ስለዚህ፣ እነዚህን ነገሮች ከሰራችሁ የተባረካችሁ ናችሁ፣ በመጨረሻው ቀን ከፍ ትላላችሁና።

፳፫ ᵐከተከለከሉት በስተቀር ስላያችኋቸው እናም ስለሰማችኋቸው ነገሮች ፃፉ።

፳፬ ወደ ፊት የሚሆን የእነዚህን ሰዎች ስራ ቀድሞ እንደነበረው አድርጋችሁ ፃፉት።

፳፭ እነሆም፣ ከተፃፉት እናም ከሚፃፉት መጽሐፍት ይህ ህዝብ ᵐይፈረድበታል፣ ምክንያቱም በእነርሱ አማካኝነት ᵃስራዎ ቻቸው ለሰዎች ይታወቃሉና።

፳፮ እናም እነሆ፣ ሁሉም ነገሮች በአብ ᵐተጽፈዋል፤ ስለዚህ በተፃፉት መጽሐፍት መሠረትም ዓለም ይፈረድበታል።

፳፯ እናም ጻድቅ በሚሆነው ለእናንተ በሰ ጠኋችሁ ፍርድ መሰረት በዚህ ህዝብ ᵐእንደ ምትፈረዱባቸው ታውቃላችሁ። ስለዚህ፣ እናንተ ምን ᵃዐይነት ሰዎች መሆን ይገባች ኋል? እውነት እላችኋለሁ ᵃእንደ እኔ ሁኑ።

፳፰ እናም እንግዲህ ᵐወደ አብ እሄዳለሁ።

፲ዕ ሀ ፩ ኔፊ ፲፩፡ ፴፪–፴፫፤ ሙሴ ፮፡ ፃ፭።
ለ ዮሐ. ፮፡ ፵ዕ፣ ፪ ኔፊ ፱፡ ፭፤ ት. እና ቃ. ፳፯፡ ፲፰።
ሐ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—ዳኛ።

፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ።

፲፮ ሀ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣ ንስሀ መግባት።
ለ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣ መጥመቅ።
ሐ ፩ ኔፊ ፲፫፡ ፴፯።
ቅ.መ.መ. መፅናት።

፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. ፍትህ።

፲፱ ሀ አልማ ፲፩፡ ፴፯።
ለ ራዕ. ፩፡ ፭፤ ፯፡ ፲ዕ፤ አልማ ፭፡ ፳፩፣ ፳፯፤ ፲፫፡ ፲፩–፲፫።
ሐ ት. እና ቃ. ፹ዕ፡ ፳ዕ። ቅ.መ.መ. እረፍት።

፳ ሀ ኤተር ፬፡ ፲፳።
ለ ቅ.መ.መ. ቅድስና።
ሐ ት. እና ቃ. ፬፡ ፪።
መ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣ መጥመቅ—አስፈላጊ።

፳፫ ሀ ፫ ኔፊ ፳፯፡ ፲–፲፯።

፳፭ ሀ ፪ ኔፊ ፴፫፡ ፲–፲፭፤ ቃላት ፩፡ ፲፩።
ለ ፩ ኔፊ ፲፭፡ ፴፪–፴፫።

፳፯ ሀ ፫ ኔፊ ፳ዕ፡ ፲፯።
ቅ.መ.መ. የሕይወት መፅሐፍ።

፳፯ ሀ ፩ ኔፊ ፲፪፡ ፱–፲፤ ሞር. ፫፡ ፲፱።
ለ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ።
ሐ ማቴ. ፭፡ ፴፰፤ ፫ ኔፊ ፲፪፡ ፴፰።

፳፰ ሀ ዮሐ. ፳፡ ፲፯።

እናም እውነት እላችኋለሁ፣ አብን ማናቸ ውንም ነገሮች በስሜ ብትጠይቁት ለእና ንተ ይሰጣችኋል።

፳፱ ስለዚህ፣ [ሀ]ለምኑ፣ እናም ይሰጣች ኋል፤ አንኳኩ እናም ይከፈትላችኋል፤ የሚጠይቅ ያገኛልና፤ እናም ለሚያንኳኳም ይከፈትለታልና።

፴ እናም እንግዲህ፣ እነሆ፣ በእናንተና ደግሞ በዚህ ትውልድ ምክንያት ሙሉ እስ ከሚሆን ድረስ ደስታዬ ታላቅ ነው፤ አዎን፣ እናም በእናንተና በዚህ ትውልድ ምክን ያት አብና ደግሞ ቅዱስ የሆኑ መላዕክቶች ሁሉ ተደስተዋል፤ ምክንያቱም ከእነርሱም ማንም [ሀ]አልጠፋምና።

፴፩ እነሆ፤ ምክንያቱም [ሀ]በዚህ ትውልድ [ለ]በህይወት ስላሉት ስለእነርሱ እንደተናገ ርኩ እንድትረዱ እፈልጋለሁ፣ እናም ማና ቸውም አይጠፉም፤ እናም በእነርሱ ሙሉ [ሐ]ደስታዬን አግኝቻለሁ።

፴፪ ነገር ግን እነሆ፣ ከዚህ ትውልድ [ሀ]አራ ተኛው ትውልድ ልክ በጥፋት ልጅም እንደ ሆነው በምርኮ ስለሚወሰዱ፣ እኔን አሳዝኖ ኛል፤ ምክንያቱም እነርሱ ለብርና ለወርቅ፣ እናም [ለ]በብልም ለሚበላሸውና ሌቦች ሊሰ ብሩትና ሊሰርቁት ለሚችሉት ይሸጡኛል። እናም በዚያን ቀን ስራቸውንም በራሳቸው ላይ በመመለስ እጎበኛቸዋለሁ።

፴፫ እናም እንዲህ ሆነ ኢየሱስ ይህ ንን ንግግሩን በጨረሰበት ወቅት ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አላቸው፥ [ሀ]በጠበበው ደጅ ግቡ፤ እናም ወደ ህይወት የሚወስ ደው ደጁ የጠበበ፣ መንገዱም የቀጠነ ስለ ሆነ፣ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸውና፤ ነገር ግን ወደ ሞት የሚወስደው ደጅ ሰፊ መንገ ዱም ትልቅ ነው፣ እናም ምሽቱ እስከሚ መጣ ሰዎችም መስራት እስከማይችሉበት ድረስ ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙ ናቸው።

ምዕራፍ ፳፰

ከአስራ ሁለቱ ደቀመዛሙርት ዘጠኙ ሲሞቱ የክርስቶስን መንግስት ለመውረስ ፈለጉ እናም ቃል ተገብቶላቸዋል—ሦስቱ ኔፋ ውያን ክርስቶስ በድጋሚ ወደ ምድር እስ ከሚመጣ በምድር ላይ ለመቆየት ፈለጉና በሞት ላይም ስልጣን ተሰጣቸው—እነር ሱም ተለውጠዋልና ሊነገሩ የማይገቡ ነገ ሮችን አዩ፣ እናም አሁን በሰዎች መካ ከል እያገለገሉ ናቸው። ከ፴፩–፴፰ ዓ.ም. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ ኢየሱስ እነዚህን ቃላት በተናገረበት ጊዜ ለደቀ መዛሙርት እንዲህ ሲል አንድ በአንድ ተናገራቸው፥ ወደ አባቴ ከሄድኩኝ በኋላ ከእኔ የምትፈ ልጉት ምንድነው?

፪ እናም ከሦስቱ በስተቀር ሌሎች በሙሉ እንዲህ ሲሉ ተናገሩ፥ አንድ ሰው በህይወት የሚቆይበትን ያህል ጊዜ ከቆየን በኋላ፣ በአ ንተም የተጠራንበት አገልግሎታችን መጨ ረሻው ሲሆን፣ በፍጥነትም ወደአንተ መን ግስትም እንመጣ ዘንድ እንፈልጋለን።

፫ እናም እርሱም አላቸው፥ ከእኔ ይህን ነገር በመፈለጋችሁ እናንተ የተባረካችሁ ናችሁ፤ ስለዚህ፣ ሰባ ሁለት ዓመት ከሆና ችሁ በኋላ ወደ መንግስቴም ትመጣላችሁ፤ እናም ከእኔ ጋር [ሀ]እረፍትንም ታገኛላችሁ።

፬ እናም እነርሱን በተናገራቸው ጊዜም፣ ወደ ሦስቱ መለስ አለና እንዲህ አላቸው፥ ወደ አባቴ ስሄድ ምን እንዳደርግላችሁ ትፈልጋላችሁ?

፭ እናም የፈለጉትንም ለእርሱ ለመናገር ባለመድፈራቸው በልባቸው አዝነው ነበር።

፮ እናም እርሱ እንዲህ አላቸው፥ እነሆ፣ ያሰባችሁትን [ሀ]አውቃለሁ፣ እናም እኔም በአይሁዶች ከመሰቀሌ በፊት በአገልግ

፳፱ [ሀ] ማቴ. ፯፡፯፤
፫ ኔፊ ፲፬፡፯።
፴ [ሀ] ዮሐ. ፲፯፡፲፪።
፴፩ [ሀ] ፫ ኔፊ ፳፯፡፳፫።
[ለ] ፫ ኔፊ ፱፡፲፩–፲፫፤ ፲፡፲፪።
[ሐ] ቅ.መ.መ. ደስታ።
፴፪ [ሀ] ፪ ኔፊ ፳፯፡፱–፲፤
አልማ ፣፭፡፲፡ ፲፪።
[ለ] ማቴ. ፮፡ ፲፱–፳፩፤
፫ ኔፊ ፲፫፡ ፲፱–፳፩።
፴፫ [ሀ] ማቴ. ፯፡ ፲፫–፲፬፤
፫ ኔፊ ፲፬፡ ፲፫–፲፬፤
ት.እና ቃ. ፳፪።
፳፰ ፫ [ሀ] ቅ.መ.መ.እረፍት።
፮ [ሀ] ዓሞ. ፪፡ ፲፫፤
አልማ ፲፯፡ ፴፪።

ሎቴ ወቅት ከእኔ ጋር የነበረውን የተወደደው ᵃዮሐንስ የፈለገውን ነገር ፈልጋችኋል።

፲ ስለዚህ፣ እናንተ ይበልጥ የተባረካ ችሁ ናችሁ፣ ᵇሞትን ᵃበጭራሽ አትቀ ምሱምና፤ ነገር ግን በአብ ፈቃድ መሰ ረት ሁሉም ነገሮች ይፈጸሙ ዘንድ በክብር በሰማይ ᶜኃይል እስከምመጣ ድረስ ለሰው ልጆች የሚያደርጋቸውን የአብን ስራዎች በሙሉ ለመመልከት ትኖራላችሁ።

፲፩ እናም የሞት ስቃይ በጭራሽ አይደር ስባችሁም፤ ነገር ግን በክብር በምመጣበት ወቅት ᵃከሟችነት ᵃሟች ወዳልሆነው በቅጽ በት ትለወጣላችሁ፤ እናም በአባቴም መን ግስት የተባረካችሁ ትሆናላችሁ።

፲፪ እናም በድጋሚ፣ በስጋ በምትቆዩ በት ወቅትም ህመምን፣ ለዓለምም ኃጢ ያት ካልሆነ በቀር ሀዘን አታውቁም፤ እናም ይህንን ሁሉ የማደርገው ከእኔ በፈለጋችሁት ነገሮች ምክንያት ነው፤ ምክንያቱም ዓለም እንዳለች በቆየችበት ወቅት ነፍሳትን ወደ እኔ ᵇለማምጣት ፈልጋችኋልና።

፲፫ እናም በዚህ የተነሳ ደስታችሁ ሙሉ ይሆናል፤ በአባቴም መንግስት ትቀመጣ ላችሁ፤ አዎን አብም ሙሉ ደስታን እንደ ሰጠኝ ᵇደስታችሁ ሙሉ ይሆናል፤ እናም እኔ እንደአባቴ እንደሆንኩ እናንተም እንደ እኔ ትሆናላችሁ፣ እናም አብና እኔም ᵃአንድ ነን፤

፲፬ እናም ᵇመንፈስ ቅዱስም ስለአብና ስለእኔ ይመሰክራል፤ አብም በእኔ የተነሳ መንፈስ ቅዱስን ለሰው ልጆች ይሰጣል።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ ኢየሱስም እነዚህን ቃላት በተናገረበት ወቅት፣ በምድር ላይ ከሚቆዩት ከሦስቱ በስተቀር፣ እያንዳንዳ ቸውን በጣቱ ነካ እናም ሔደ።

፲፮ እናም እነሆ፣ ሰማያት ተከፈቱና፣ እነ ርሱ ወደሰማይ ᵇተነጠቁና ለመነገር የማ ይችሉ ነገሮችን ተመለከቱ፣ እናም ሰሙ።

፲፯ እናም እንዳይናገሩም ᵇተከልክለው ነበር፤ የተመለከቷቸውንና የሰሟቸውን ነገ ሮች ለመናገር እንዲችሉ ስልጣንም አልተ ሰጣቸውም፤

፲፰ እናም በስጋም ሆነ ከስጋ ውጪ መሆ ናቸውን ለማወቅ አልቻሉም፤ የእግዚአብ ሔር የሆኑትን ነገሮች ለመመልከት እንዲ ችሉ ለእነርሱ ከስጋዊ ሰውነት ሟች ወዳ ልሆነው ሰውነት ᵇየተለወጡ መሰላቸው።

፲፱ ነገር ግን እንዲህ ሆነ በድጋሚ በም ድረ ገጽ ላይ ያገለግሉ ነበር፤ ይሁን እንጂ በሰማይ በተሰጣቸው ትዕዛዝ ምክንያት ስለ ሰሙአቸው እናም ስለተመለከቱአቸው ነገ ሮች አላስተማሩም።

፲፳ እናም እንግዲህ፣ ከተለወጡበት ጊዜ ጀምሮ ሟችም ሆኑ የማይሞቱ እኔም አላ ውቅም፤

፲፳፡ ነገር ግን በተሰጡት ታሪክ መሰረት ይህን ያህል አውቃለሁ—እናም ህዝቡን ሁሉ በማስተማር፣ በሰበካቸው የሚያምኑ ብዙዎችን ከቤተክርስቲያኗ ጋር በማቀላ ቀል፣ በማጥመቅ በምድር ገጽ ተጉዘዋል፣ እናም የተጠመቁም ሁሉ መንፈስ ቅዱስን ተቀብለዋል።

፲፳፪ እናም ከቤተክርስቲያኗ ባልሆኑት ወደ ወህኒ ተጥለዋል። እናም ሁለት ቦታም በመ ከፈላቸው ᵇእስር ቤቶቹም ሊይዟቸው አል ቻሉም።

፲፳፫ እናም ወደ ምድርም ውስጥ ተጣሉ፤ ነገር ግን ምድሪቱንም በእግዚአብሔር ቃል መቱ፤ በዚህም ᵇበኃይሉ ከመሬቱ ጥልቅ ድነው ነበር፤ እናም እነርሱን በበቂ ሁኔታ ሊይዝ የሚችል ጉድጓድ ለመቆፈር አል ቻሉም።

፲ ለ ዮሐ. ፳፩፡፳፩–፳፫፣ ት. እና ቃ. ፯፡፩–፬።
፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. የተቀየሩ ሰዎች።
ለ ፬ ኔፊ ፩፡፲፬፣ ሞር. ፰፡፲–፲፩፣ ኤተር ፲፪፡፲፣ ፲፯።
ሐ ፣ ኔፊ ፳፡፳፪።
፲፪ ሀ ፣ ኔፊ ፳፰፡፲፯–፴።
ቅ.መ.መ. ስጋዊ፣ የሚሞት።
ለ ቅ.መ.መ. የማይሞት፣ አለሟችነት።
፲፫ ሀ ፊልጵ. ፩፡፳፣–፳፬፣ ት. እና ቃ. ፯፡፩–፯።
፲፬ ሀ ት. እና ቃ. ፹፬፡፴፯–፴፰።
ለ ዮሐ. ፲፯፡፳–፳፣።
፲፭ ሀ ፣ ኔፊ ፴፩፡፲፣ ፴፯–፴፱፣
፣ ኔፊ ፲፩፡፴፪።
፲፣ ሀ ፣ ፪ ቆሮ. ፣፪፡፪–፬።
፲፡ ሀ ት. እና ቃ. ፫፯፡፲፣–፲፣፣፯።
፲፩ ሀ ሙሴ ፩፡፲፩።
ቅ.መ.መ. መለወጥ።
፲፪ ሀ የሐዋ. ፣፯፡ ፳፣፣ አልማ ፣፡፡፡ ፳፣፣–፳፣፣።
፲፫ ሀ ሞር. ፣፡ ፳፡፡።

፳፩ እናም ሦስት ጊዜም ᐟበእቶኑ ውስጥ ተወረወሩ፣ እናም ምንም ጉዳት አልደረሰባቸውም።

፳፪ እናም ሁለት ጊዜ ᐟበዱር አውሬ ዋሻ ተጣሉ፤ እናም እነሆ ልጅ ከሚጠባ የበግ ጠቦትጋር እንደሚጫወተው ከአውሬዎች ጋር ይጫወቱ ነበር፣ እናም ምንም ጉዳት አልደረሰባቸውም።

፳፫ እናም እንዲህ ሆነ በኔፊ ሰዎች መካከል ሔዱና፣ በምድረ ገጽ ላይም ለሁሉም ሰዎች የክርስቶስን ᐟወንጌል አስተማሩ፤ እናም እነርሱ ወደ ጌታ ተለወጡና፣ ከክርስቶስ ቤተክርስቲያንም ጋር ተቀላቀሉ፣ እንደ ኢየሱስ ቃልም ᐞያ ትውልድ በሙሉ እንደዚህ ተባርኮ ነበር።

፳፬ እናም እንግዲህ እኔ ሞርሞን፣ ለጊዜው እነዚህን ነገሮች በተመለከተ ንግግሬን አቆማለሁ።

፳፭ እነሆ፣ ሞትን ቀምሰው የማያውቁትን ሰዎች ᐟስማቸውን ልፅፍ ነበር፣ ነገር ግን ጌታ ከለከለኝ፤ ስለዚህ ከዓለም ተደብቀዋልና ስማቸውን አልጽፍም።

፳፮ ነገር ግን እነሆ፣ እኔ አይቻቸዋለሁ፣ እናም እኔንም አስተምረውኛል።

፳፯ እናም እነሆ ከአህዛብ መካከል ይሆናሉ፣ አህዛብም አያውቋቸውም።

፳፰ ደግሞም ከአይሁዶች መካከል ይሆናሉ፣ እናም አይሁዶችም አያውቋቸውም።

፳፱ እናም እንዲህ ይሆናል፣ ፍላጎታቸው ይሟላ ዘንድና ደግሞም በውስጣቸው ባለው አሳማኝ በሆነው የእግዚአብሔር ኃይል ምክንያት፣ ጌታ በጥበቡ ብቁ መሆኑን በሚመ ስለው፣ ᐟለተበተኑት የእስራኤል ነገዶች በሙሉና፣ ለሁሉም ሀገር፣ ነገድ፣ ቋንቋና ህዝብ ያገለግላሉ፣ እናም ደግሞ ከመካከላቸው ብዙ ነፍሳትን ወደ ኢየሱስ ያመጣሉ።

፴ እናም እነርሱም እንደ እግዚአብሔር ᐟመላዕክቶች ናቸው፤ እናም በኢየሱስ ስም ወደ አብ ከጸለዩ መልካም በሚመስላቸው ለማንኛውም ሰው እራሳቸውን ለማሳየት ይችላሉ።

፴፩ ስለዚህ፤ ሰዎች ሁሉ በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት በእርግጥ መቆም ከሚገባቸው ᐟከታላቁ እና ከሚመጣው ቀን በፊት፣ ታላቅ እንዲሁም ድንቅ ስራዎች በእነርሱ ይከናወናሉ፤

፴፪ አዎን ከፍርድ ቀን በፊት እንኳን በአህዛብ መካከል በእነርሱ አማካኝነት ᐟታላቅ እና ድንቅ ስራ ይሰራል።

፴፫ እናም የክርስቶስን ድንቅ ስራዎች ታሪክ በሙሉ የሚናገሩት ቅዱሳን መጻሕፍት ካሉአችሁ፣ በክርስቶስ ቃላት መሰረት እነዚህ ነገሮች በእርግጥ እንደሚመጡ ታውቃላችሁ።

፴፬ እናም የኢየሱስንና ደግሞ እርሱ ᐟየመረጣቸውንና በመካከላቸው የላካቸውን ቃላት ᐞለማያዳምጡ ወዮላቸው፤ የኢየሱስን ቃላትና የላካቸውን ቃላት የማይቀበሉ እርሱንም አይቀበሉም፤ እናም ስለዚህ እርሱም በመጨረሻው ቀን አይቀበላቸውም፤

፴፭ እናም እነርሱ ባይወለዱ ይሻላቸው ነበር። ደህንነት ለማምጣት በሰዎች እግር ስር ᐟየተረገጠውን እግዚአብሔር ቁጣ ፍርድ ለማስወገድ ይቻላል ብላችሁ ትገምታላችሁን?

፴፮ እናም እንግዲህ እነሆ፣ ጌታ ስለመረጣቸው፣ አዎን፣ በሰማያት ስለተወሰዱት ስለሦስቱ፣ እንደተናገርኩት ከሟችነት ወደ ማይሞተው መንፃታቸውን አላውቅም—

፴፯ ነገር ግን እነሆ፣ ከጻፍኩት በኋላ ጌታን ስለእነርሱ ጠይቄዋለሁ እና ለእኔም በሰውነታቸው ላይ ለውጥ መደረጉ አስፈላጊ መሆኑን አለበለዚያም ሞትን መቅመስ እንዳለባቸው ገልፆልኛል፤

፳፩ ᐟ ዳን. ፫፡ ፳፪–፳፯፤ ፬ ኔፊ ፩፡ ፴፪።
፳፪ ᐟ ዳን. ፮፡ ፲፯–፳፫፤ ፬ ኔፊ ፩፡ ፴፫።
፳፫ ᐟ ቅ.መ.መ. ወንጌል። ᐞ ፫ ኔፊ ፳፯፡ ፴–፴፩።
፳፭ ᐟ ፫ ኔፊ ፲፱፡ ፱።
፳፱ ᐟ ቅ.መ.መ. እስራኤል— የተበተኑት እስራኤል፤ እስራኤል—የጠፉት የእስራኤል አስር ጎሳዎች።
፴ ᐟ ቅ.መ.መ. መላእክት።
፴፩ ᐟ ሔለ. ፲፪፡ ፳፭፤ ፫ ኔፊ ፳፯፡ ፱–፭።
፴፪ ᐟ ፫ ኔፊ ፳፯፡ ፲–፲፯።
፴፫ ᐟ ቅ.መ.መ. ነቢይ። ᐞ ኤተር ፱፡ ፳–፲፪።
፴፭ ᐟ ሔለ. ፲፪፡ ፪።

፳፯ ስለዚህ፣ ሞትን እንዳይቀምሱ፣ በዓ ለም ኃጢያት ካልሆነ በቀር በህመም ሆነ በሀዘን እንዳይሰቃዩ በሰውነታቸው ላይ ᵐለውጥ ተደርጓል።

፳፰ እንግዲህ ይህ ለውጥ በመጨረሻው ቀን ከሚከናወነው ለውጥ ጋር እኩል አይ ደለም፤ ነገር ግን ሰይጣን በእነርሱ ላይ ስል ጣን እንዳይኖረው፣ እነርሱንም ᵐመፈተን እንዳይቻለው፣ ለውጥ በእነርሱ ላይ ተደ ርጓል፤ እናም በስጋቸው ᵃተቀድሰዋል፣ ሐቅዱስም ነበሩ እናም የምድርም ኃይላ ትም እነርሱን ለመያዝ አይቻላቸውም።

፳ እናም የክርስቶስ የፍርድ ቀንም እስከ ሚመጣ በዚህ ሁኔታ ይቆያሉ፤ እናም በዚ ያን ቀንም ታላቅ ለውጥን ይቀበሉና ከዚህ በኋላም ከአብ መንግስትም ላለመውጣት ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር በሰማያት ለዘ ለዓለም ለመኖር ይቀበላሉ።

ምዕራፍ ፳፱

የመፅሐፈ ሞርሞን መምጣት ጌታ እስ ራኤልን የሚሰበስብበት እንዲሁም ቃል ኪዳኑን ለመፈጸም የሚጀምርበት ምል ክት ነው—የኋለኛው ቀን ራዕዮችን እን ዲሁም ስጦታዎችን የማይቀበሉ የተረገሙ ይሆናሉ። ከ፳፩–፳፭ ዓ.ም. ገደማ።

፩ እናም እንግዲህ እነሆ፣ እንዲህ እላች ኋለሁ፤ እነዚህ ነገሮች በቃሉ መሰረት ወደ አህዛብ ᵐመምጣታቸው በጥበቡ ጌታ ተገቢ መሆናቸውን በሚመለከትበት ጊዜ፣ አብም ከእስራኤል ልጆች ጋር በድጋሚ ወደ ትው ልድ ምድራቸው ለመመለስ ᵃቃል ኪዳን የገባውን መፈፀም እንደጀመረ ታውቃላ ችሁ።

፪ እናም በቅዱሳን ነቢያት የተነገሩት የጌታ ቃልም በሙሉ እንደሚፈፀሙ ታው ቃላችሁ፤ እናም ጌታ ወደ እስራኤል ልጆች የሚመጣበት ጊዜውን ᵐአዘገየ ማለት አያስ ፈልጋችሁም።

፫ እናም የተነገሩት ቃላትም ከንቱ ናቸው ብላችሁ በልባችሁ አትገምቱ፣ ምክንያቱም እነሆ ጌታ ለእስራኤል ቤት ለህዝቡ የገባውን ቃል ኪዳን ያስታውሳልና።

፬ እናም እነዚህ የተባሉት በመካከላችሁ ሲመጡ በምትመለከቱበት ጊዜ፣ ከዚያም የጌታን ስራ ልትወቅሱ አይገባችሁም፣ ምክንያቱም ᵐየፍትህ ᵃጎራዴ በቀኝ እጁ ናትና፤ እናም እነሆ፣ በዚያን ቀን ስራውን የምትወቅሱ ከሆነ በቅርቡይህችም እንድ ታሸንፋችሁ ያደርጋል።

፭ የጌታን ስራ ᵐየሚወቅስ ᵃወዮለት፣ አዎን፣ ክርስቶስን እና ስራዎቹን ᵐለሚ ክድ ወዮለት!

፮ አዎን፣ የጌታን ራዕይ ለሚክድ፣ እናም ጌታ ከእንግዲህ በራዕይ፣ ወይንም በትን ቢት፣ ወይም ᵐበስጦታ፣ ወይም በልሳን ወይም በፈውስ፣ ወይንም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አይሰራም ለሚል ᵃወዮለት!

፯ አዎን፣ እናም በዚያን ቀን ᵐጥቅምን ለማግኘት፣ በኢየሱስ ክርስቶስም ከእንግ ዲህ ᵃድንቅ ነገር አይሰራም ለሚል ወዮ ለት፤ ይህንን የሚያደርግ ᵐእንደጥፋት ልጅ ይሆናልና፣ ለእርሱም በክርቶስ ቃል መሰ ረት ምህረት አይኖረውምና!

፰ አዎን፣ እናም ከእንግዲህ ᵐልታጉረመ ርሙ፣ እንዲሁም ᵃልትወቅሱ፣ ᵐአይሁ ዶችንም ሆነ፣ የእስራኤል ቤት ቅሪት በሆ ኑት ላይ ትቀልዱም ዘንድ አይገባችሁም፤ እነሆም ጌታ ለእነርሱ የገባውን ቃል ኪዳን

፳፰ ᵇ ቅ.መ.መ. የተቀየሩ ሰዎች።
፳፱ ᵃ ቅ.መ.መ. መፈተን፣ ፈተና።
ᵇ ቅ.መ.መ. ቅድስና።
ᶜ ቅ.መ.መ. ቅድስና።
፳፱ ᵃ ᵍ ኔፊ ፴፡–፫፡፡
ᵇ ሞር. ፭፡–፲፩፣ ፳፡
ᶜ ᵃ ሉቃ. ፲፪፡–፴፭፡፡
ᵈ ᵃ ቅ.መ.መ. ፍትህ።
ᵉ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᶠ ᵃ ሞር. ፡–፲፩፡–፲፭፡
ᵍ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵃ ᵍ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵇ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᶜ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵃ ᵍ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵇ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᶜ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵃ ᵍ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵇ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᶜ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵃ ᵍ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵇ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᶜ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵃ ᵍ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵇ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᶜ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵃ ᵍ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵇ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᶜ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵃ ᵍ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵇ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᶜ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵃ ᵍ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵇ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᶜ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵃ ᵍ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵇ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᶜ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵃ ᵍ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵇ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᶜ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵃ ᵍ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵇ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᶜ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵃ ᵍ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵇ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᶜ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵃ ᵍ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵇ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᶜ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵃ ᵍ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵇ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᶜ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵃ ᵍ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵇ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᶜ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵃ ᵍ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵇ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᶜ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵃ ᵍ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵇ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᶜ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵃ ᵍ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵇ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᶜ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵃ ᵍ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵇ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᶜ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵃ ᵍ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵇ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᶜ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵃ ᵍ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵇ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᶜ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵃ ᵍ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᵇ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡
ᶜ ᵃ ᵍ ኔፊ ፳፡–፳፡

ያስታውሳል፣ እናም በመሃላ እንደገባውም
ይፈጽምላቸዋል።
፱ ስለዚህ ጌታም ለእስራኤል ቤት የገባ
ውን ቃል ኪዳን ለማሟላት ፍትሁን ለመ
ፈጸም እንዳይችል ቀኝ እጁን ወደግራው
ለመመለስ ይቻለናል በማለት መገመት የለ
ባችሁም።

ምዕራፍ ፴

የኋለኛው ቀን አህዛብ ንሰሃ እንዲገቡ፣ እናም ወደ ክርስቶስ እንዲመጡ፣ እና ከእስራኤል ቤትም ጋር እንዲቆጠሩ ታዘዋል። ከ፴፬–፴፭ ዓ.ም. ገደማ።

፩ እናንት አህዛብ ሆይ፣ ስሙ፤ እናም
እናንተን በተመለከተ እንድናገር ሀያዘዘኝን
ህያው የሆነው የእግዚአብሔር ልጅ የኢየ
ሱስ ክርስቶስን ቃላት አድምጡ፤ እነሆም
እንዲህ ብዬም እንድፅፍ አዞኛል፥
፪ ሀአህዛብ ሁሉ ከኃጢያት መንገዳችሁ
ተመለሱ፤ እናም ከክፉ ስራዎቻችሁ፣
ከውሸታችሁና፣ ከአታላይነታችሁ፣ እናም
ከዝሙት ተግባራችሁና፣ በድብቅ ከምት
ፈፅሙት ርኩሰት፣ በጣዖት ማምለካች
ሁም፣ ከግድያችሁም፣ ከካህናት ተንኮላ
ችሁም፣ ከምቀኝነታችሁም፣ ከፀበኝነታ
ችሁም፣ እናም ከሁሉም ኃጢአቶቻችሁና
ርኩሰታችሁ ሁሉ ለንሰሃ ግቡ፣ እናም ለኃ
ጢአቶቻችሁ ስርየትን ትቀበሉና፣ በመን
ፈስ ቅዱስ ትሞሉ ዘንድ፣ የእስራኤል ቤት
ከሆኑት ህዝቦቼ ጋርም ሐትቆጠሩ ዘንድ ወደ
እኔ ኑ፣ እናም በስሜ ተጠመቁ።

አራተኛው ኔፊ
የኔፊ መፅሐፍ

ከኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርት አንዱ የነበረው የኔፊ ልጅ

በእርሱ መዛግብት መሰረት የነበረው የኔፊ ህዝብ ታሪክ።

ኔፋውያን እንዲሁም ላማናውያን ሁሉ ወደ ጌታ ተለወጡ—ሁሉም ነገሮች በጋራ ነበሯቸው፣ ተአምራትን ሰሩ፣ በምድሪቱም ላይ በለፀጉ—ከሁለት መቶ ዓመታት በኋላ፣ መከፋፈል፣ ክፋት፣ ሀሰተኛ ቤተ ክርስቲያኖች፣ እናም ስደት ተነሳ—ከሦስት መቶ ዓመታት በኋላ፣ ኔፋውያን እንዲሁም ላማናውያን ኃጢአተኞች ሆኑ—አማሮንም ቅዱሳን መጻሕፍቶችን ደበቃቸው። ከ፴፭–፫፻፳፩ ዓ.ም. ገደማ።

እናም እንዲህ ሆነ ሠላሳ አራተኛው ዓመ
ትና፣ ደግሞ ሠላሳ አምስተኛው ዓመት
አለፈ፣ እናም እነሆ የኢየሱስ ደቀመዛሙ
ርት በምድሪቱ ዙሪያ በሁሉም ስፍራ የክ
ርስቶስን ቤተክርስቲያን መሰረቱ። እናም
ወደ እነርሱ የመጡት፣ ለኃጢአታቸውም
ከልባቸው ንሰሃ የገቡት ሰዎች ሁሉ በኢየ
ሱስ ስም ተጠመቁ፣ እናም ደግሞ መንፈስ
ቅዱስን ተቀበሉ።
፪ እናም እንዲህ ሆነ በምድሪቱ ገፅ የነበ
ሩት ላማናውያንም ሆኑ ኔፋውያን በሙሉ
በሠላሳ ስድስተኛው ዓመት ወደ ጌታ ተለ
ወጡና፣ በመካከላቸው ፀብም ሆነ ጥላቻ
አልነበረም፣ እናም እያንዳንዱ ሰው እርስ
በርሱ በቅን ይሰራ ነበር።

፴፩ ሀ ፫ ኔፊ ፳፥ ፲፪–፲፫።
፪ ሀ ቅ.መ.መ. አህዛቦች።
ለ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣ ንስሀ
መግባት።
ሐ ገላ. ፫፥ ፳፯–፳፱፤
፪ ኔፊ ፲፥ ፲፰–፲፱፤
፫ ኔፊ ፲፮፥ ፲–፲፫፤
፳፩፥ ፳፪–፳፫፤
አብር. ፪፥ ፲።

፫ እናም ᵐሁሉም ነገሮች በጋራ ነበሩአ
ቸው፣ ስለዚህ ድሃና ሃብታም፣ ግዙተኛና ነፃ
አልነበረም፣ ነገር ግን ሁሉም ነፃና፣ ሰማያ
ዊውን ስጦታ ተቀባይ ነበሩ።

፬ እናም እንዲህ ሆነ ሠላሳ ሠባተኛውም
ዓመት ደግሞ አለፈ፣ እናም በምድሪቱ
ሠላም ሰፈነ።

፭ እናም በኢየሱስ ደቀመዛሙርት አማካ
ኝነት ታላቅና ድንቅ ሥራዎች ይሰሩ ነበር፣
ስለዚህ ህመምተኞችን ᵐይፈውሱ፣ እናም
ሙታኖችን ያስነሱና፣ ሽባውን እንዲራ
መድ ያደርጉ፣ እናም ዐይነ ስውር ብርሃን
እንዲያገኝና፣ ደንቆሮ እንዲሰማ ያደርጉ
ነበር፤ እናም ሁሉንም አይነት ᵃታዕምራቶ
ችን በሰው ልጆች መካከል ያከናውኑ ነበር፤
እናም በክርስቶስ ስም ካልሆነ በቀር በማንም
ታምራቶችን አልሰሩም።

፮ እና በዚህ ሠላሳ ስምንተኛው ዓመት
አለፈና፣ ደግሞ ሠላሳ ዘጠነኛው፣ እናም
አርባ አንደኛውና፣ አርባ ሁለተኛው ዓመት
አለፈ፣ አዎን፣ አርባ ዘጠነኛው ዓመት እስ
ከሚያልፍ ድረስና፣ ደግሞ ሃምሳ አንደኛ
ውና፣ ሃምሳ ሁለተኛው፤ አዎን፣ እናም
ሃምሳ ዘጠነኛው ዓመትም እስከሚያልፍ
ድረስ እንዲህ ሆነ።

፯ እናም ጌታ በምድሪቱ ላይ እጅግ እንዲ
በለፅጉ አደረጋቸው፤ አዎን፣ በዚህም የተ
ነሳ ከተሞች በተቃጠሉበት ሥፍራ ከተሞ
ችን በድጋሚ አቋቋሙ።

፰ አዎን፣ ያቺን ታላቋን ᵐየዛራሔምላ
ከተማንም በድጋሚ እንድትገነባ አደረጉ።

፱ ነገር ግን ᵐየሰጠሙ ብዙ ከተሞች ነበሩ፣
እናም በቦታውም ውሃ ይፈልቅ ነበር፤ ስለ
ዚህ እነዚህ ከተሞች ሊታደሱ አልተቻላ
ቸውም።

፲ እናም አሁን፣ እነሆ፣ እንዲህ ሆነ የኔፊ
ህዝቦች ተጠናከሩ፣ እናም በጣም በፍጥ
ነት ተባዙና፣ እጅግ ᵐመልካም እንዲሁም
ያማሩ ህዝቦች ሆኑ።

፲፩ እናም ተጋቡና፣ ለጋብቻም ተሰጡ፣
እናም ጌታ በብዙ በገባላቸው ቃል ኪዳ
ኖች ተባረኩ።

፲፪ እናም ከእንግዲህ በሙሴ ᵐህግ ᵃስራ
ዎችና ሥርዓት መሠረት አልተራመዱም፣
ሥርዓቶቹንም አይከተሉም ነበር፤ ነገር ግን
ከጌታቸውና ከአምላካቸው በተቀበሉአቸው
ትዕዛዛት፣ ያለማቋረጥ ᵃበᵇማቸውና፣ በፀ
ሎታቸው፣ እንዲሁም በየወቅቱ ለመፀለይና
የጌታን ቃል ለመስማት በመሰብሰብ ይራ
መዱ ነበር።

፲፫ እናም እንዲህ ሆነ በምድሪቱ ህዝ
ቦች መካከል ሁሉ ምንም ፀብ አልነበረም፤
ነገር ግን በኢየሱስ ደቀመዛሙርት መካከል
ኃያል የሆኑ ተአምራት ይሰሩ ነበር።

፲፬ እናም እንዲህ ሆነ ሰባ አንደኛው እን
ዲሁም ሰባ ሁለተኛው ዓመት አለፈ፤
አዎን፣ በአጠቃላይ ሰባ ዘጠነኛው ዓመት
አለፈ፤ አዎን መቶ ዓመታት አለፉ፣
እናም ኢየሱስ በምድር እንዲቆዩ ከመ
ረጣቸው ᵐከሦስቱ በስተቀር ሁሉም የኢ
የሱስ ደቀመዛሙርት ወደ እግዚአብሔር
ᵃገነት ሄደዋል፤ እናም በእነርሱም ቦታ
ᵐየተሾሙ ሌሎች ᵐደቀመዛሙርት ነበሩ፤
እናም ደግሞ የዚያም ትውልድ ብዙዎች
ሞቱ።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ በህዝቡ ልብ ውስጥ
ባለው የእግዚአብሔር ፍቅር የተነሳ በምድ
ሪቱ ᵐፀብ አልነበረም።

፲፮ እናም ᵐቅናት፣ ቁጣ፣ ሁከት፣
ዝሙት፣ መዋሸትም፣ ግድያም ሆነ ᵃዝሙ
ትን የሚቀሰቅስ ምንም ነገር አልነበረም፤
እናም በእርግጥ በእግዚአብሔር እጅ ከተፈ

፩ ፫ ᴴ የሐዋ. ፬፡ ፴፪፤
ፍ. ኔፊ ፳፯፡ ፲፱።
ቅ.መ.መ. መቀደስ፣ የቅድስና
ህግ።
፭ ᴴ ቅ.መ.መ. መፈወስ፣
ፈውሶች።
ᵃ ዮሐ. ፲፬፡ ፲፪።
ቅ.መ.መ. ተአምራት።
፳ ᴴ ፫ ኔፊ ፳፡ ፳።
፴ ᴴ ፫ ኔፊ ፴፡ ፩፣ ፯።
፲ ᴴ ሞር. ፴፡ ፮።
፲፪ ᴴ ቅ.መ.መ. የሙሴ ህግ።
ᵃ ፪ ኔፊ ፳፭፡ ፴፣
ፍ ኔፊ ፲፭፡ ፪–፳።
ᵇ ሞሮኒ ፮፡ ፭፣
ት. እና ታ. ፹፰፡ ፷፯–፷፯።
፲፭ ᴴ ፫ ኔፊ ፳፡ ፳።
ᵐ ቅ.መ.መ. ሐዋ. ፲፡ ፲–፲፱።
ᵐ ቅ.መ.መ. ገነት።
ᵐ ቅ.መ.መ. መሾም፣ ሹመት።
ᵐ ቅ.መ.መ. ደቀ መዛሙርት።
፲፮ ᴴ ቅ.መ.መ. ሰላም።
፲፯ ᴴ ቅ.መ.መ. አንድነት።
ᵐ ቅ.መ.መ. ምኞት።

ጠሩት ሰዎች መካከል እንደዚህ ያለ ᵐደስ ተኛ ሊሆን የቻለ ህዝብ አልነበረም።

፲፯ ሌቦችም ሆኑ ገዳዮች፣ ላማናውያ ንም ሆኑ ማንኛውም ዓይነት በመደብ የተ ለዩ ሰዎች አልነበሩም፤ ነገር ግን ሁሉም ᵐበአንድነት የክርስቶስ ልጆች፣ እናም የእ ግዚአብሔርንም መንግስት ወራሾች ነበሩ።

፲፰ እናም እነርሱ እንዴት የተባረኩ ነበሩ! ምክንያቱም ጌታ በስራዎቻቸው ሁሉ ባር ኳቸዋልና፤ አዎን፣ አንድ መቶ አስረኛው ዓመት እስኪያልፍ እንኳን ተባርከዋል፤ በልፅገዋልም፤ እናም ከክርስቶስ ጉብኝት ጀምሮ የመጀመሪያው ትውልድ አልፎአ ልና፣ በምድሪቱ ሁሉ ፀብ አልነበረም።

፲፱ እናም እንዲህ ሆነ ይህንን የመጨ ረሻ መዝገብ ጠብቆ ያቆየው (እናም ᵐበኔፊ ሠሌዳዎች ላይ ነበር ያስቀመጣቸው) ኔፊ ሞተና ልጁ አሞፅ በእርሱ ቦታ አስቀመ ጠው፤ እናም አሞፅም ደግሞ በኔፊ ሠሌ ዳዎች ላይ ጠበቃቸው።

፳ እናም ለሰማንያ አራት ዓመታት አስ ቀመጠው፣ እናም በቤተክርስቲያኑ ላይ ከተነሱትና የላማናውያንን ስም ከወሰዱት ጥቂት ሰዎች በቀር በምድሪቱ አሁንም ሠላም ነበር፤ ስለዚህ በምድሪቱ ላይ በድ ጋሚ ላማናውያን ሆኑ።

፳፩ እናም እንዲህ ሆነ አሞፅም ደግሞ ሞተ (እናም ይህ ክርስቶስ ከመጣ ከመቶ ዘጠና አራት ዓመት በኋላ ነበር) እናም ልጁ አሞፅ በእርሱ ምትክ መዛግብቱን ጠበቀ፤ እናም ደግሞ በኔፊ ሠሌዳዎች ላይ ጠበቃ ቸው፤ እናም ይህም ደግሞ ይህ መፅሐፍ በሆነው በኔፊ መጽሐፍ ላይ ተፅፈው ነበር።

፳፪ እናም እንዲህ ሆነ ሁለት መቶ ዓመ ታት አለፉ፤ እናም ከጥቂቶች በስተቀር ሁለተኛውም ትውልድ በሙሉ አለፈ።

፳፫ እናም እንግዲህ እኔ ሞርሞን፣ ህዝቡም እንደተባዙ፣ በምድሪቱ ገፅ ላይ በሙሉ እስከተሰራጩ ና፣ በክርስቶስ ባገ ኙት ብልፅግናም እጅግ ሀብታሞች እንደ ሆኑ እንድታውቁ እፈልጋለሁ።

፳፬ እናም አሁን፣ በሁለት መቶ አንደ ኛው ዓመት በመካከላቸው ᵐበኩራት የተወ ጣጠሩ፣ ይኸውም ውድ ልብሶችንና መል ካም ዕንቁ ከሆኑት ሁሉ እንዲሁም የዓለምን መልካም የሆኑ ነገሮችን የሚለብሱ ነበሩ።

፳፭ እናም ከዚያን ጊዜ በኋላ በመካከላ ቸው ᵐየጋራ የሆኑ ዕቃዎች እንዲሁም ንብ ረቶች አልነበሯቸውም።

፳፮ እናም በመደብ መከፋፈል ጀመሩ፤ እናም ለራሳቸው ᵐጥቅም ሲሉ ᶮቤተክርስ ቲያን መስራት ጀመሩ፤ እናም የክርስቶስን እውነተኛ ቤተክርስቲያንም መካድ ጀመሩ።

፳፯ እናም እንዲህ ሆነ ሁለት መቶ አስ ረኛው ዓመት እንዳለፈም በምድሪቱ ብዙ ቤተክርስቲያኖች ነበሩ፤ አዎን፣ ክርስቶስ ንም እናውቃለን የሚሉ ብዙ ቤተክርስቲያ ኖችም ነበሩ፤ እናም ይሁን እንጂ የወንጌሉን አብዛኛውን ክፍል ᵐክደዋል፣ በዚህም የተ ነሳ ሁሉንም ዓይነት ክፋቶች ተቀብለዋል፤ እናም እርሱ ብቁ ባለመሆኑ ᶮየተከለከለውን ቅዱስ የሆነውን ሰጥተዋልና።

፳፰ እናም በክፋታቸውም የተነሳና ልባቸ ውን በተቆጣጠረው በሰይጣን ኃይል የተነሳ ይህች ᵐቤተክርስቲያን እጅግ ተስፋፋች።

፳፱ እናም በድጋሚ፣ ክርስቶስን የሚክድ ሌላ ቤተክርስቲያን ነበር፤ እናም በትህት ናቸውና በክርስቶስ ባላቸው እምነት የተ ነሳ እውነተኛ የሆነችውን የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን ᵐአሳደዱ፤ እናም በመካከላቸው ብዙ ተአምራትንም በመስራታቸው ጠሉ ዋቸው።

፲፯ *ሐ* ሞዛያ ፪፡ ፵፩፤ አልማ ፯፡ ፳፫።
ቅ.መ.መ. ደስታ።
፲፯ *ሀ* ዮሐ. ፲፯፡ ፳፩።
ቅ.መ.መ. ፅዮን።
፲፱ *ሀ* ቅ.መ.መ. ሰሌዳዎች።
፳፬ *ሀ* ቅ.መ.መ. ኩራት።
፳፭ *ሀ* ፬ ኔፊ ፩፡ ፫።
፳፯ *ሀ* ት. እና ቃ. ፲፡ ፶፯።
ቅ.መ.መ. የካህን ተንኮል።
ለ ፩ ኔፊ ፳፪፡ ፳፫፤ ፪ ኔፊ ፳፰፡ ፫፤ ሞር. ፰፡ ፴፪–፴፰።
፳፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. ክህደት።
ለ ፫ ኔፊ ፲፰፡ ፳፰–፳፱።
፳፰ *ሀ* ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ— የዲያብሎስ ቤተክርስቲያን።
፳፱ *ሀ* ቅ.መ.መ. ማሳደድ፣ መሳደድ።

፴ ስለዚህ ከእነርሱ ጋር በቀሩት የኢየ
ሱስ ደቀመዛሙርት ላይ ኃይልና ስልጣ
ናቸውን ተጠቀሙ፣ ᵐወህኒ ቤትም ጣሉ
አቸው፤ ነገር ግን በውስጣቸው ባለው በእ
ግዚአብሔር ቃል ኃይል ወህኒ ቤቱ ሁለት
ቦታ ተከፈለ፣ እናም በመካከላቸው ኃያል
ተአምራትን መስራት ቀጠሉ።

፴፩ ይሁን እንጂ፣ እናም እነዚህ ሁሉ አስ
ደናቂ ነገሮች ቢኖሩም እንኳን፣ ሰዎቹ ልባ
ቸውን አጠጥረው ነበር፣ እናም በኢየሩሳ
ሌም የነበሩት አይሁዶች በቃሉ መሠረት
ኢየሱስን ለመግደል እንደፈለጉት ሁሉ እነ
ርሱን ለመግደል ፈለጉ።

፴፪ እናም ᵐበእሳት ᶣዓምድም ውስጥ
ጣሉአቸውና፣ ምንም ጉዳት ሳይደርስባ
ቸው ወጡ።

፴፫ እናም ደግሞ በዱር አራዊት ᵐዋሻ
ጣሉአቸውና፣ እነሆ ልጅ ከሚጠባ የበግ
ጠቦትጋር እንደሚጫወተው ከአውሬዎች
ጋር ይጫወቱ ነበር፣ እናም ምንም ጉዳት
ሳይደርስባቸው ከመካከላቸው ወጡ።

፴፬ ይሁን እንጂ፣ ሰዎቹ በብዙ ካህናትና
ሃሰተኛ ነቢያት ብዙ ቤተክርስቲያኖችን
እንዲሰሩና ሁሉንም አይነት ክፋቶች እን
ዲሰሩ በመመራታቸው ልባቸውን አጠጥ
ረውት ነበር። እናም የኢየሱስን ህዝቦችንም
ᵐመቱ፤ ነገር ግን የኢየሱስ ሰዎች መልሰው
አልመቱአቸውም ነበር። እናም ከዓመት
ዓመት፣ ሁለት መቶ ሰላሳ ዓመት እስከሚ
ያልፍ ድረስ እምነት በማጣትና በክፋቶቻ
ቸው መነመኑ።

፴፭ እናም እንግዲህ እንዲህ ሆነ በዚሁ
ዓመት፤ አዎን፣ በሁለት መቶ ሠላሳ አን
ደኛው ዓመት፣ በህዝቡ መካከል ታላቅ የሆነ
መከፋፈል ነበር።

፴፮ እናም እንዲህ ሆነ በዚህ ዓመት ነፋ
ውያን ተብለው የሚጠሩ ሰዎች ተነሱና፣
እነርሱም በክርስቶስ እውነተኛ አማኞች
ነበሩ፤ እናም በመካከላቸው በላማናው
ያን—ያዕቆባውያንና፣ ዮሴፋውያን፣ እናም
ዞራማውያን ተብለው የሚጠሩ ነበሩ፤

፴፯ ስለዚህ በክርስቶስ እውነተኛ አማ
ኞች እናም የክርስቶስ እውነተኛ አምላኪ
ዎች (ከእነርሱም መካከል በምድር የቀሩት
ሦስቱ የኢየሱስ ᵐደቀመዛሙርት ነበሩ) ነፋ
ውያንና፣ ያዕቆባውያን፣ እናም ዮሴፋው
ያንና፣ ዞራማውያን ተብለው ይጠሩ ነበር።

፴፰ እናም እንዲህ ሆነ ወንጌሉን ያልተቀ
በሉት ላማናውያን፣ ልሙኤላውያንና፣ እስ
ማኤላውያን ተብለው ይጠሩ ነበር፤ እናም
እምነት አጥተው አልመነመኑም፣ ነገር ግን
በክርስቶስ ወንጌል ላይ በፈቃደኝነት ᵐአምፀ
ዋል፤ እናም አባቶቻቸው ከመጀመሪያው
ጀምረው እንደመነመኑት፣ እነርሱ ልጆቻ
ቸውን እንዳያምኑ አስተምረዋቸዋል።

፴፱ እናም ይህም የነበረው ከመጀመሪያም
እንደነበረው የአባቶቻቸው ክፋትና ርኩስ
ነት ምክንያት ነው። እናም ከጥንት ጀምሮ
ላማናውያን የኔፊን ልጆች እንዲጠሉ ᵐእን
ደተማሩት የእግዚአብሔርን ልጆች እንዲ
ጠሉ ተማሩ።

፴ እናም እንዲህ ሆነ ሁለት መቶ አርባ
አራተኛው ዓመት አለፈ፣ እናም የህዝቡም
ጉዳይ እንዲህ ነበር። እናም ከህዝቡ ይበል
ጡን ክፉ የነበሩት የበረቱ ሆኑና፣ ከእግዚ
አብሔር ሰዎች ይበልጥ እጅግ ብዙ ሆኑ።

፴፩ እናም አሁንም ለራሳቸው ቤተክር
ስቲያንን መስራት ቀጠሉ፣ በከበሩ ነገሮ
ችም አስጌጡአቸው። በዚህም ሁለት መቶ
ሃምሳ ዓመት፣ እናም ደግሞ ሁለት መቶ
ስልሳ ዓመታትም አለፉ።

፴፪ እናም እንዲህ ሆነ ክፉዎች የሆኑት
የጋድያንቶን ቡድኖች ሚስጥር መሃላንና
ᵐውህደትን በድጋሚ መገንባት ጀመሩ።

፴፫ እናም ደግሞ የኔፊ ህዝብ ተብለው
የሚጠሩት እጅግ ሀብታሞች በመሆናቸው

፴ ᶣ ፫ ነሬ ፳፰፡ ፲፱–፳፡
፴፪ ᶣ ዳን. ፫፡ ፳፯–፳፱፡
ለ ፫ ነሬ ፳፰፡ ፳፩፡
፴፫ ᶣ ፫ ነሬ ፳፰፡ ፳፪፡
፴፬ ᶣ ፫ ነሬ ፲፪፡ ፴፱፤
ት. እና ቃ. ፶፰፡ ፳፫–፳፯፡
፴፭ ᶣ ፫ ነሬ ፳፰፡ ፮–፯፤
ሞር. ፰፡ ፲–፲፩፡
፴፮ ᶣ ቅ.መ.መ. አመጽ፡
፴፱ ᶣ ሞዛያ ፲፡ ፲፯፡
፴፪ ᶣ ቅ.መ.መ. የሚስጥር ስብሰባ፡

መኩራት ጀመሩ፣ እናም እንደወንድሞቻ
ቸው እንደላማናውያን ከንቱ ሆኑ።
፵፬ እናም ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ደቀመዛሙ
ርቱም ስለዓለም [ሀ]ኃጢያት ማዘን ጀመሩ።
፵፭ እናም እንዲህ ሆነ ሦስት መቶ ዓመ
ታት ካለፉ በኋላ፣ የኔፊ እንዲሁም የላማና
ውያን ሰዎች በተመሳሳይ ሁኔታ እጅግ ክፉ
ዎች ሆኑ።
፵፮ እናም እንዲህ ሆነ የጋድያንቶን ዘራፊ
ዎች በምድሪቱ ገፅ ሁሉ ተሰራጩ፤ እናም
ከኢየሱስ ደቀመዛሙርት በቀር ፃድቅ የነ
በረ ማንም አልነበረም። እናም በመጋዘኖ
ቻቸው በርካታ ወርቆችንና ብሮችን አከማ
ችተው ነበር፣ እናም ማንኛውንም ሸቀጦቻ
ቸውን ይገበያዩ ነበር።
፵፯ እናም እንዲህ ሆነ ሦስት መቶ አም
ስት አመታት ካለፉ በኋላ፣ (እናም ህዝቡ
አሁንም በክፋታቸው ቀጥለዋል) አሞፅ
ሞተ፤ ወንድሙ አማሮንም መዛግብቱን
በእርሱ ምትክ ጠበቀ።
፵፰ እናም እንዲህ ሆነ ሦስት መቶ ሃያ
ኛው ዓመት ካለፈ በኋላ፣ አማሮን በመን
ፈስ ቅዱስ በመገፋፋቱ፣ ቅዱስ የሆኑትን
[ሀ]መዛግብት ደበቀ—አዎን፣ ቅዱሳን የነበ
ሩትን ከትውልድ እስከ ትውልድ ሲተላ
ለፉ የመጡትን መዝገቦች ሁሉ—ክርስቶስ
ከመጣ ከሦስት መቶ ሀያ ዓመት ጀምሮ ያሉ
ትን ጭምር ደበቀ፤
፵፱ እናም በጌታ ትንቢትና ቃል ኪዳን
መሰረት [ሀ]በድጋሚ ወደ ያዕቆብ ቤት ቅሪት
ይመጡ ዘንድ በጌታ ደበቃቸው። እናም
የአማሮን መዝገብ ፍፃሜ ይህ ነው።

መፅሐፈ ሞርሞን

ምዕራፍ ፩

አማሮን ስለቅዱሳን መዛግብት ለሞርሞን መመሪያዎችን ሰጠው—በኔፋውያን እና በላማናውያን መካከል ጦርነት ተጀመረ—ሦስቱ ኔፋውያን ተወሰዱ—ክፋት፣ አለማመን፣ አስማትና ጥንቆላ ሰፈነ። ከ፫፻፳፩–፫፻፳፮ ዓ.ም. ገደማ።

እናም እንግዲህ እኔ [ሀ]ሞርሞን፣ ስላየኋ
ቸውና ስለሰማኋቸው ነገሮች [ለ]ታሪክ
ፃፍኩ፣ እናም መፅሐፈ ሞርሞን ብዬ ጠራ
ሁት።
፪ እናም [ሀ]አማሮን በጌታ መዛግብቱን ሊደ
ብቅ ባለበት ጊዜ፣ ወደ እኔ መጣ፣ (እኔም
አስር ዓመቴ ስለነበርና ሕዝቦቼ እንደተ
ማሩት በመጠኑ [ለ]መማር ጀመርኩ) እናም
አማሮን እንዲህ አለኝ፥ እንደምገምተው
አንተ አስተዋይ እንዲሁም ያስተማሩህን
በፍጥነት የምትረዳ ልጅ ነህ፤
፫ ስለዚህ፣ ሃያ አራት ዓመት ሲሆንህ ስለ
ነዚህ ሰዎች የተመለከትካቸውን ነገሮች እን
ድታስታውስ እፈልጋለሁ፤ እናም በዚያም
ዕድሜም ስትደርስ [ሀ]ሺም ተብላ በምትጠራ
ኮረብታ ወደ አንቱም ምድር ሂድ፤ እናም
በዚያ ይህንን ሕዝብ በተመለከተ ቅዱስ
የሆኑ የተፃፉትን ሁሉ በጌታ እዚያ ደብቄ
አቸዋለሁ።
፬ እናም እነሆ፣ [ሀ]የኔፊን ሠሌዳዎች ለራስህ
ትወስዳለህና የተቀሩትን በነበሩበት ሥፍራ
ትተዋቸዋለህ፤ ስለነዚህ ሰዎች የተመለከ
ትካቸውን ነገሮች በሙሉ በኔፊ ሠሌዳ ላይ
ትፅፋለህ።
፭ እናም እኔ ሞርሞን፣ [ሀ]የኔፊ ዘርያ በመ
ሆኔ (እናም የአባቴም ስም ሞርሞን ነበር)

፵፬ሀ ፫ ኔፊ ፳፰፥፱።
፵፰ሀ ሔለ. ፫፥፲፫፣ ፲፭–፲፮።
፵፱ሀ ኢኖስ ፩፥፲፫።

[ሞርሞን]

፩ ፩ሀ ቅ.መ.መ. ሞርሞን፣ የኔፋውያን ነቢይ።
ለ ፫ ኔፊ ፭፥፲፩–፲፰።
፪ሀ ፬ ኔፊ ፩፥፵፯–፵፱።
ለ ሞዛያ ፩፥፫–፭።

፫ሀ ኤተር ፱፥፫።
፬ሀ ቃላት ፩፥፩፣ ፲፩። ቅ.መ.መ. ሰሌዳዎች።
፭ሀ ፫ ኔፊ ፭፥፲፪፣ ፳።

አማሮን ያዘዘኝን ነገሮች በሙሉ አስታወ ስኩ።

፮ እናም እንዲህ ሆነ አስራ አንድ አመት ሲሆነኝ፣ በምድሪቱ በስተደቡብ በኩል እስከ ዛራሄምላ ምድርም በአባቴ ተወሰ ድኩኝ።

፯ ምድሪቱ በሙሉ በህንፃ ተሸፍናለች፣ እናም ህዝቡም እንደባህር አሸዋ በቁጥር በዝተው ነበር።

፰ እናም እንዲህ ሆነ በዚህ ዓመት ኔፋው ያንና፣ ያዕቆባውያን፣ እናም ዮሴፋውያ ንና፣ ዞራማውያን ባሉበት በኔፋውያን መካ ከል ጦርነት ተጀመረ፤ እናም ይህም ጦር ነት በኔፋውያንና፣ በላማናውያንም፣ በል ሙኤላውያን፣ እንዲሁም በእስማኤላው ያን መካከል ነበር።

፱ እንግዲህ ላማናውያንና፣ ልሙኤላው ያን፣ እናም እስማኤላውያን፣ ላማናውያን ተብለው ይጠሩ ነበር፣ እናም ሁለቱ ቡድ ኖችም ኔፋውያን እናም ላማናውያን ነበሩ።

፲ እናም እንዲህ ሆነ ጦርነቱም በሲዶም ውሃ በዛራሔምላ ዳርቻ በመካከላቸው ተጀ መረ።

፲፩ እናም እንዲህ ሆነ ኔፋውያን ሠላሳ ሺህ እስከሚበልጡ ብዙ ቁጥር ያላቸውን ሰዎች በአንድነት ሰበሰቡ። እናም እንዲህ ሆነ በዚሁ ዓመትም ብዙ ጦርነቶች ነበሩአ ቸው፣ በዚህም ኔፋውያንም ላማናውያንን አሸነፉአቸውና ብዙዎችን ገደሉአቸው።

፲፪ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን ዕቅ ዳቸውን ተዉና፣ በምድሪቱም ላይ ሠላም ነበር፤ እናም ለአራት ዓመታት ሠላም ሰፍኗል፣ ስለዚህ ምንም ደም መፋሰስ አልነበረም።

፲፫ ነገር ግን ኃጢያት በምድሪቱ ገፅ ላይ ሠፈነ፣ በዚህም የተነሳ ጌታ [ሀ]የተወደዱ ደቀመዛሙርቱን ወሰደ፣ እናም በህዝቡም ክፋት የተነሳ የተዓምር ሥራና ፈውስ ቆመ።

፲፬ እናም ከጌታም ምንም ዐይነት [ሀ]ስጦ ታዎች አልነበሩም፣ እናም በክፋቶቻቸው እናም [ለ]ባለማመናቸው የተነሳ [ሐ]መንፈስ ቅዱስ በማንም ላይ አልመጣም ነበር።

፲፭ እናም አስራ አምስት ዓመት ሲሆነ ኝና ጥቂት አስተዋይ በመሆኔ በጌታ ተጎብ ኝቼ ነበር፣ እናም የኢየሱስን ቸርነት ቀምሼ አውቄም ነበር።

፲፮ እናም ይህን ሕዝብ ለመስበክ ጥረት አደርግ ነበር፣ ነገር ግን አንደበቴ ተዘጋና፣ እንዳልሰብክላቸውም ተከልክዬ ነበር፤ ምክንያቱም እነሆ ወደው በአምላካቸው ላይ [ሀ]አምፀው ነበርና፤ እናም በክፋታቸው የተነሳ የተወደዱ ደቀመዛሙርት ከምድ ሪቱ [ለ]ተወስደዋል።

፲፯ ነገር ግን እኔ በመካከላቸው ቀረሁ፣ ነገር ግን በልባቸው ጠጣርነት ምክንያት እንዳልሰብክላቸው ተከለከልኩ፤ እናም በልባቸው ጠጣርነት የተነሳ ምድሪቱ [ሀ]ተረ ግማ ነበር።

፲፰ እናም እነዚህ ከላማናውያን መካከል የነበሩት የጋድያንቶን ዘራፊዎች፣ ምድ ሪቱን ወረሩአት፤ በዚህም የተነሳ በዚያን ሥፍራ ይኖሩ የነበሩት [ሀ]ህብቶቻቸውን በመሬት ውስጥ ቀበሩ፤ እናም ለመያዝ እን ዳይችሉና በድጋሚ እንዳይዙ ወይም እንዳ ያገኙ ጌታ ምድሪቷን ስለረገማት እነዚህም የማይጨበጡ ሆኑ።

፲፱ እናም እንዲህ ሆነ መናፍስትን ጠሪ ዎችና ጠንቋዮች፣ እንዲሁም አስማተ ኞች ነበሩ፤ እናም የአቢናዲና ደግሞ የላ ማናዊው ሳሙኤል ቃል ሁሉ እስከሚፈ ፀም የክፉው ሥልጣን በምድሪቱ ገፅ ሁሉ ላይ ይሰራ ነበር።

ምዕራፍ ፪

ሞርሞን የኔፊን ሠራዊት መራ—ምድሪ ቱን ደም እና እልቂት ጠረጋት—ኔፋው ያን እንደተኮነነ አይነት ሀዘን አለቀሱ እናም

፲፫ ሀ ፫ ኔፊ ፳፫፡፪፣ ፲፪።
፲፬ ሀ ሞሮኒ ፣፡ ፰–፲፰፣ ፳፬።
ለ ቅ.መ.መ. አለማመን።
ሐ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. አመጽ።
ለ ሞር. ፰፡ ፣።
፲፯ ሀ ፪ ኔፊ ፭፡ ፣–፲፡ አልማ ፶፭፡ ፣–፲፡ ፣ ፲፯።
፲፰ ሀ ሔለ. ፣፡ ፣፰–፳፣ ኤተር ፣፡ ፡–፪።

አዘኑ—የፀጋ ጊዜአቸውም ያለፈ ነው—ሞርሞን የኔፊን ሠሌዳ ወሰደ—ጦርነትም ቀጠለ። ከ፫፻፳፯–፫፻፵ ዓ.ም. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ በዚያው ዓመት በኔፋውያንና በላማናውያን መካከል በድጋሚ ጦርነት ሆነ። እናም ወጣት ብሆንም እንኳን በአቋሜ ትልቅ ነበርኩ፤ ስለዚህ የኔፊ ሕዝብ መሪያቸው እንዲሁም የሠራዊቶቻቸው መሪ እንድሆን ሾሙኝ።

፪ ስለዚህ እንዲህ ሆነ በአስራ ስድስተኛው ዓመቴ በላማናውያን ላይ የኔፋውያን የጦሩ መሪ በመሆን ሔድኩ፤ ስለዚህ ሦስት መቶ ሃያ ስድስት ዓመታት አለፉ።

፫ እናም እንዲህ ሆነ በሦስት መቶ ሃያ ሰባተኛው ዓመት ላማናውያን እጅግ ታላቅ በሆነ ኃይል በእኛ ላይ መጡ፤ በዚህም የተነሳ ወታደሮቼን አስፈራሩአቸው፤ ስለዚህ እነርሱም አልተዋጉም፣ እናም በስተሰሜን ወዳሉት ሀገሮችም ማፈግፈግ ጀመሩ።

፬ እናም እንዲህ ሆነ ወደ አንጎላ ከተማ መጣንና፣ ከተማዋንም ወሰድን፣ እናም እራሳችንን ከላማናውያን ለመከላከል ዝግጅት አደረግን። እናም እንዲህ ሆነ፣ በጉልበታችን ያህችን ከተማ ምሽጋችን አደረግናት፤ ነገር ግን ምንም እንኳን ምሽጋችን እንዲህ ቢሆንም ላማናውያን በእኛ ላይ መጡና ከከተማዋ አባረሩን።

፭ እናም ደግሞ ከዳዊት ምድርም አባረሩን።

፮ እናም እኛም ዘመትንና፣ በባሕሩ ዳርቻ በስተሰምዕራብ ጫፍ ወደሚገኘው ወደ ኢያሱ ምድር መጣን።

፯ እናም እንዲህ ሆነ ህዝባችንን በአንድ ላይ እንዲሆን እናደርግ ዘንድ በተቻለ ፍጥነት በአንድነት ተሰበሰብን።

፰ ነገር ግን እነሆ፣ ምድሪቱ በዘራፊዎች እንዲሁም በላማናውያን ተሞልታ ነበር፤ እናም ታላቅ ጥፋት በህዝቤ ላይ የተመዘዘ ቢሆንም፣ ስለክፉ ስራዎቻቸው ንስሃ አልገቡም፣ ስለዚህ በኔፋውያንና ደግሞ በላማናውያን በኩል በምድሪቱ ገፅ ሁሉ ደም መፋሰስና እልቂት ሆነ፤ እናም በምድሪቱ ላይ ህዝቡ በህግና በስርዓት ላይ ያምፅ ነበር።

፱ እናም እንግዲህ፣ ላማናውያን ንጉስ ነበራቸው፣ ስሙም አሮን ይባል ነበር፤ እናም ከአርባ አራት ሺህ ወታደሮቹ ጋር በእኛ ላይ መጣ። እናም እነሆ፣ በአርባ ሁለት ሺዎች ተቋቋምኩት። እንዲህም ሆነ ከፊቴ እስኪሸሽ በሠራዊቴ አሸነፍኩት። እናም እነሆ፣ ይህ ሁሉ ተፈፅሟል፣ ሦስት መቶ ሠላሳ ዓመታትም አለፉ።

፲ እናም እንዲህ ሆነ ኔፋውያን ለክፋታቸው ንስሃ መግባት ጀመሩና፣ በነቢዩ ሳሙኤል እንደተተነበየው መጮህ ጀመሩ፤ እነሆ በሌቦቹና በዘራፊዎች፣ እናም በገዳዮቹና፣ በአስማተኞች፣ እንዲሁም በምድሪቱ ባሉት ጠንቋዮች የተነሳ ማንም ሰው የራሱ የሆነውን ለመጠበቅ አልተቻለውምና።

፲፩ በእነዚህ ነገሮች ምክንያት በምድር በሙሉ፣ በተለይ ከሌሎቹ በበለጠ በኔፊ ሕዝብ መካከል፣ ሀዘን እናም ልቅሶ ሆነ።

፲፪ እናም እንዲህ ሆነ እኔ ሞርሞን፣ በጌታ ፊት ለቅሶአቸውንና ሀዘናቸውን በተመለከትኩ ጊዜ፣ የጌታን ምህረት እንዲሁም ታጋሽነት በማወቅም፣ ስለዚህ ጌታ እንደገና ፃድቃን ይሆኑ ዘንድ ለእነርሱ መሃሪ እንደሆን በመገመቴ፣ ልቤ በውስጤ ሀሴት ማድረግ ጀመረች።

፲፫ ነገር ግን እነሆ ደስታዬ ከንቱ ነበር፣ ምክንያቱም [ሀ]ሀዘናቸው በእግዚአብሔር ቸርነት ለንስሃ አልነበረምና፤ ነገር ግን [ለ]የባለኩነኔ ሀዘን ነበር ምክንያቱም ጌታ ሁልጊዜም በኃጢያት [ሐ]ደስታን እንዲቀበሉ አልፈቀደላቸውም ነበር።

፲፬ እናም በተሰበረ [ሀ]ልብና በተዋረደ መንፈስ ወደ ኢየሱስም አልመጡም፤ ነገር ግን እግዚአብሔርን [ለ]ይረግሙታል እናም ሞትን ይመኛሉ። ይሁን እንጂ በህይወት ለመቆየት በጎራዴአቸው ይታገላሉ።

፪ ፲፫ሀ ፪ ቆሮ. ፯፥ ፲፤ አልማ ፵፪፥ ፳፱።
ለ ቅ.መ.መ. ኩነኔ።
ሐ አልማ ፵፩፥ ፲።
፲፬ሀ ቅ.መ.መ. የተሰበረ ልብ።
ለ ቅ.መ.መ. መስደብ።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ ሀዘኔም በድጋሚ ወደ እኔ ተመለሰ፣ በጊዜያዊም እንዲ ሁም በመንፈሳዊ ᵐየጸጋ ᵃቀናቸው ሐማለ ፋን ተመልክቻለሁ፤ በሺዎች የሚቆጠሩት በገሃድ በአምላካቸው ላይ በማመፃቸው፣ ሲገደሉና እንደፍግ ሰውነታቸው በመሬት ላይ ሲቆለል ተመልክቻለሁና። እና በዚሁ ሦስት መቶ አርባ አራት ዓመት አለፈ።

፲፮ እናም እንዲህ ሆነ በሦስት መቶ አርባ አምስተኛው ዓመትም ኔፋውያን ከላማና ውያን ፊት መሸሽ ጀመሩ፤ እናም ሲያ ፈገፍጉም እነርሱን ማቆም ከመቻሉ በፊት በያሾን ምድር እስከሚመጡ ድረስ ተከተ ሉአቸው።

፲፯ እናም እንግዲህ፣ የጄሽን ከተማ አማሮንም መዛግብቱ እንዳይጠፋ ለጌታ ያስቀመጠበት ᵐምድር አጠገብ ነበር። እናም እነሆ አማሮን እንዳዘዘኝ አደረግሁና፣ የኔ ፊን ሠሌዳ ወሰድኩኝ፣ እናም አማሮን እን ዳዘዘኝ ታሪኩን ፃፍኩኝ።

፲፰ እናም በኔፊ ሠሌዳ ላይ ስለክፋቶችና ስለ ርኩሰቶች በሙሉ ታሪክን ፃፍኩ፤ ነገር ግን የሰዎችን ባሕሪይ ለማየት ከቻልኩበት ዕድሜዬ ጀምሮ በዐይኔ የማያቋርጥ ክፋትና ርኩሰትን በመመልከቴ በነዚህ ᵐሠሌዳዎች ላይ ስለክፋታቸውና ርኩሰታቸው የነበረ ውን ታሪክ በሙሉ ከመፃፍ ተቆጥቤ ነበር።

፲፱ እናም በክፋቶቻቸው የተነሳ ለእኔም ወዮልኝ፣ ምክንያቱም በዘመኔ ሁሉ በክፋ ታቸው የተነሳ ልቤ በሀዘን ተሞልታለችና፤ ይሁን እንጂ፣ በመጨረሻው ቀን ᵐከፍ እን ደምል አውቀዋለሁ።

፳ እናም እንዲህ ሆነ በዚያ ዓመትም የኔ ፊን ሰዎች ታድነውና ተባርረው ነበር። እናም እንዲህ ሆነ የሺም ምድር ተብላ በም ትጠራም በስተሰሜን እስከምንወጣ ድረስ ተባረርን።

፳፩ እናም እንዲህ ሆነ የሺምን ከተማ ምሽግ አደረግናትና፣ ሕዝባችንን ከጥፋት እናድን ዘንድ በሚቻለው መጠን በአንድ ላይ ሰበሰብን።

፳፪ እናም እንዲህ ሆነ በሦስት መቶ አርባ ስድስተኛው ዓመት በድጋሚ ወደ እኛ መምጣታቸውን ጀመሩ።

፳፫ እናም እንዲህ ሆነ ሕዝቤ በላማናው ያን ፊት በድፍረት እንዲቆሙና፣ ለሚስ ቶቻቸውና፣ ለልጆቻቸው፣ ለመኖሪያቸ ውና ለቤታቸው ᵐእንዲዋጉ በታላቅ ሀይል ተናገርኩአቸው፣ እናም አበረታኋቸው።

፳፬ እና ቃሌም በጥቂቱ አበረታታቸው፣ በዚህም የተነሳ ከላማናውያን ፊት አል ሸሹም ነበር፣ ነገር ግን በፊታቸው በድፍ ረት ቆመው ነበር።

፳፭ እናም እንዲህ ሆነ ከሠላሳ ሺህ ወታ ደሮቻችን ጋር ነበር ከሃምሳ ሺህ ወታደሮች ጋር የገጠምነው። እናም እንዲህ ሆነ በፊ ታቸው በፅናትም ቆምን እነርሱም ከፊታ ችን ሸሹ።

፳፮ እናም እንዲህ ሆነ በሸሹ ጊዜ ከወታ ደሮቻችን ጋር ተከተልናቸው፣ እናም በድ ጋሚ አገኘናቸውና አሸነፍናቸው፤ ይሁን እንጂ የጌታ ብርታት ከእኛ ጋር አልነበረም፤ አዎን፣ የጌታ መንፈስ ከእኛ ጋር ስላልነበረ በብቻችን ነበርን፣ በዚህም፤ ስለዚህ ልክ እንደ ወንድሞቻችን ደካሞች ሆነን ነበር።

፳፯ እናም በህዝቦቼም ክፋትና ርኩሰት የተነሳ በደረሰው ታላቅ መቅሰፍት ልቤ አዝና ነበር። ነገር ግን እነሆ፣ በላማናው ያንና በጋድያንቶን ዘራፊዎች ላይ የትው ልድ ምድራችንን በድጋሚ እስከምንወስድ ድረስ ሄድን።

፳፰ እናም ሦስት መቶ አርባ ዘጠነኛው ዓመት አለፈ። እናም በሦስት መቶ ሃምሳ ኛው ዓመት ከላማናውያንና ከጋድያንቶን ዘራፊዎች ጋር ስምምነት አደረግንና፣ የት ውልድ ምድራችንንም ተከፋፈልን።

፳፱ እናም ላማናውያን በስተሰሜን በኩል ያለውን መሬት ሰጡን፤ አዎን፣ ᵐበቀጭኑ

፲፭ ᵐ ቅ.መ.መ. ጸጋ።
ᵃ ሔሌ. ፲፫፡ ፴፰።
ᵇ ኤር. ፰፡ ፳፡
ት. እና ቃ. ፶፮፡ ፲፮።

፲፯ ᵐ ሞር. ፩፡ ፩–፬።
፲፰ ᵐ ቅ.መ.መ. ሰሌዳዎች።
፲፱ ᵐ ሞዛያ ፳፫፡ ፳፪፣
ኤተር ፬፡ ፲፱።

፳፫ ᵐ ሞዛያ ፳፡ ፲፭፤
አልማ ፶፫፡ ፶፭።
፳፱ ᵐ አልማ ፳፪፡ ፴፪።

ማለፊያ ወደ ምድሪቱ ደቡብ የሚያመራ ውን ጭምር። እናም ለላማናውያን በምድ ሪቱ በስተደቡብ ያለውን ሁሉ ሰጠናቸው።

ምዕራፍ ፫

ሞርሞን ለኔፋውያን ስለንሰሃ ጮኸ—እነ ርሱም ታላቅ ድልን አገኙ እናም በራሳ ቸው ብርታት ተመኩ—ሞርሞን እነርሱን አልመራም አለ፣ እናም ለእነርሱ የነበረው ፀሎትም በእምነት አልነበረም—መፅሐፈ ሞርሞን አሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች በወንጌል እንዲያምኑ ይጋብዛል። ከ፫፻፲፰–፫፻፲፰፪ ዓ.ም. ገደማ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን አሥር ተጨማሪ ዓመታት አስከሚያልፍ ድረስ በድጋሚ ለመዋጋት አልተመለሱም። እናም እነሆ፣ ምድሪቱንና የጦር መሳሪያ ዎችን ለጦርነት ጊዜ እንዲያዘጋጁ የሕዝ ቦቼ ኔፋውያን ጉልበታቸውን ተጠቀምኩ።

፪ እናም እንዲህ ሆነ ጌታ እንዲህ ሲል ተናገረኝ፥ ለዚህ ሕዝብ ጩኽ—ንሰሃ ግቡና፣ ወደእኔ ኑ፣ እናም ተጠመቁና፣ ቤተክርስቲያኔን በድጋሚ ሥሩ፣ እናም ትድናላችሁ።

፫ እናም ለዚህ ሕዝብ ጮህኩ፣ ነገር ግን በከንቱ ነበር፤ እናም እነርሱም ጌታ እንዳ ዳናቸውና ለንሰሃም ዕድል የሰጣቸው እርሱ እንደነበር አልተረዱም። እናም እነሆ በጌታ በአምላካቸውም ላይ ልባቸውን አጠጥረ ውት ነበር።

፬ እናም እንዲህ ሆነ ይህ አስረኛው ዓመት፣ በአጠቃላይ ክርስቶስ ከመጣ ሦስት መቶ ስልሳ ዓመት ካለፈ በኋላ የላማናውያን ንጉሥ ደብዳቤ ላከልኝ፣ ይኸውም እነርሱ ከእኛ ጋር ለጦርነት በድጋሚ ለመምጣት እንደሚዘጋጁ እንዳውቅ ነበር።

፭ እናም እንዲህ ሆነ ሕዝቤንም በዳርቻው ባለችው ከተማ በቀጭኑ ማለፊያ በምድሪቱ በስተደቡብ በኩል በሚወስደው ወደ ወደ መችው ምድር በአንድነት እራሳቸውን እን ዲሰበስቡ አደረግሁ።

፮ እናም ላማናውያን ማንኛውንም ምድ ራችንን እንዳይወስዱብን ወታደሮቻቸውን እናስቆማቸው ዘንድ ሠራዊታችንን እዚያ አስቀመጥን፤ ስለዚህ ባለን ኃይል ሁሉ ተጠቅመን መሸግንባቸው።

፯ እናም እንዲህ ሆነ በሦስት መቶ ስልሳ አንደኛው ዓመት ላማናውያን ከእኛ ጋር ለመዋጋት ወደ ወደመችው ከተማ ወረዱ፤ እናም እንዲህ ሆነ በዚያን ዓመት በድጋሚ ወደራሳቸው ምድር እስኪመለሱ አሸነፍ ናቸው።

፰ እናም በሦስት መቶ ስልሳ ሁለተኛው ዓመት በድጋሚ ለመዋጋት መጡ። እናም በድጋሚ አሸነፍናቸውና፣ ብዙ ቁጥር ያላ ቸውንም ገደልናቸው፣ ሙታኖቻቸውም ወደ ባሕር ተጣሉ።

፱ እናም እንግዲህ፣ ህዝቤ ኔፋውያን ባደ ረጉት በዚህ ታላቅ ነገር፣ በጉልበታቸው *ተኩራሩና በሰማያት ፊትም በጠላቶቻቸው የተገደሉትን የወንድሞቻቸውን ደም እንደ ሚበቀሉ መማል ጀመሩ።

፲ እናም ከጠላቶቻቸው ጋር *ለመዋጋትና ከምድረገፅም እነርሱን ለማጥፋት በሰማያ ትና ደግሞ በእግዚአብሔር ዙፋን መሀላን አደረጉ።

፲፩ እናም እንዲህ ሆነ እኔ፣ ሞርሞን፣ በዚህ ህዝብ ክፋትና እርኩሰት የተነሳ ከእ ንግዲህ የዚህ ህዝብ አዛዥና መሪ በፍጹም አልሆንም አልኩኝ።

፲፪ እነሆ፣ እነርሱን መርቼ ነበር፣ ኃጢአ ተኞች ቢሆኑም በብዙ ጊዜ በጦርነት መራ ኋቸውና፣ በውስጤ ባለው በእግዚአብ ሔር *ፍቅር ከልቤ በሙሉ ወደድኳቸው፤ እናም ቀኑን ሙሉ ነፍሴ ለአምላኬ ስለእ ነርሱ ፀሎትን ታፈስ ነበር፤ ይሁን እንጂ፣ ልባቸውን በማጠጠራቸው ይህ *በእምነት አልነበረም።

፲፫ እናም ለሦስት ጊዜም ከጠላቶቻቸው

፫ ፱ *ሀ* ፪ ኔፊ ፩፡ ፴፱።
፲ *ሀ* ፫ ኔፊ ፫፡ ፳–፳፩፤
ሞር. ፩፡ ፱።
፲፪ *ሀ* ቅ.መ. ፍቅር።
ለ ሞር. ፭፡ ፪።

እጅ አስለቅቄአቸዋለሁ፣ እናም እነርሱ ለጋጢአቶቻቸው ንሰሃ አልገቡም ነበር።

፲፬ በጌታችንና በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ ᵐየተከለከሉትን በሙሉ በማሉ ጊዜ፣ እናም ከጠላቶቻቸው ጋር ለመዋጋትና የወንድሞቻቸውን ደም እራሳቸው ሊበቀሉ በሚሄዱበት ጊዜ፣ እነሆ የጌታ ድምፅ ወደ እኔም እንዲህ ሲል መጣ፥

፲፭ ᵐበቀል የእኔ ነው፣ እናም ራሴ ᵃእከፍ ለዋለሁ፤ እናም ምክንያቱም ይህ ሕዝብ እኔ ካዳንኳቸው በኋላ ንሰሃ ስላልገቡ፣ እነሆ፣ እነርሱ ከምድረ ገፅ ይጠፋሉ።

፲፮ እናም እንዲህ ሆነ በድጋሚም ጠላቶቼ ላይ ለመሄድ በጥብቅ ተቃወምኩ፤ ልክ ጌታ እንዳዘዘኝ አደረግሁም፤ እናም ስለሚመጡት ነገሮች ስለመሰከረው የመንፈስ መገለጥ መሰረት፣ ስላየኋቸውና ስለሰማኋቸው ነገሮች ለዓለም ለመግለፅ ብቸኛ ምስክር በመሆን ቆምኩኝ።

፲፯ ስለዚህ ᵐለእናንተ ለአህዛብና ደግሞ ሥራው በሚጀመርበት ጊዜ ወደ ትውልድ ምድራችሁ ለመመለስ ለምትዘጋጁት የእስራኤል ቤት ለሆናችሁት እጽፋለሁ፤

፲፰ አዎን፤ እነሆ፣ ለሁሉም ለዓለም ዳርቻ፣ አዎን፣ በኢየሩሳሌም ምድር ኢየሱስ በመረጣቸው በአስራ ሁለቱ ደቀመዛሙርት እንደስራችሁ ᵐወደሚፈረድባችሁ ወደ እናንተ አስራ ሁለት የእስራኤል ነገዶች እጽፋለሁ።

፲፱ እናም በዚህች ምድር ኢየሱስ በመረጣቸው ᵐበአስራ ሁለቱ ወደሚፈረድባቸው የሕዝቦች ቅሪት ደግሞ እጽፋለሁ፤ እናም እነርሱም ኢየሱስ በኢየሩሳሌም በመረጣቸው ይፈረድባቸዋል።

፳ እናም እነዚህን ነገሮች መንፈስ ለእኔ ይገልፅልኛል፤ ስለዚህ ለሁላችሁም እጽፋለሁ። በዚህም ምክንያት ሁላችሁም፣ አዎን፣ የአዳም ᵐቤተሰብ የሆኑት እያንዳንዱ ነፍስ በክርስቶስ ᵃየፍርድ ወንበር ፊት መቆም እንዳለባችሁ እንድታውቁ እጽፋለሁ፤ እናም መልካምም ይሁን መጥፎ እንደስራችሁ እንዲፈረድባችሁ መቆም አለባችሁ።

፳፩ እናም ደግሞ በመካከላችሁ በሚሆነው የክርስቶስን ወንጌል ᵐታምኑ ዘንድ፤ እናም ደግሞ የጌታ ቃል ኪዳን ሕዝብ የሆኑት ᵃአይሁዶች ከተመለከቱት፣ እናም ከሰሙት፣ ከገደሉት ከኢየሱስ በተጨማሪ፣ ᵃየጥንቱ ክርስቶስና የጥንቱ አምላካቸው እንደነበረ ሌላ ᵐምስክር ይኖራቸዋል።

፳፪ እናም በዓለም ዳርቻ ያላችሁ ᵐሁሉ ንሰሃ እንድትገቡና በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ለመቆም እንድትዘጋጁ ለማሳመን እፈልጋለሁ።

ምዕራፍ ፬

ጦርነትና እልቂት ቀጠለ—ጋጥአን ጋጥአንን ይቀጣሉ—በእስራኤል ሁሉ ከዚህ በፊት ከነበረው የበለጠ ታላቅ ክፋት ሠፈነ—ሴቶችና ልጆች ለጣዖት መስዋዕት ሆኑ—ላማናውያን ኔፋውያንን ከፊታቸው መጥረግ ጀመሩ። ከ፫፻፳፯ ፫–፫፻፴፩ ዓ.ም. ገደማ።

፩ እናም እንግዲህ እንዲህ ሆነ በሦስት መቶ ስልሳ ሦስተኛው ዓመት ኔፋውያን ከወደመው ምድር ወጥተው ከላማናውያን ጋር ለመዋጋት ከሠራዊታቸው ጋር ሄዱ።

፪ እናም እንዲህ ሆነ የኔፋውያን ሠራዊቶች በድጋሚ ወደ ወደመችው ምድር ተገፍተው ተመለሱ። እናም በደከሙበት ጊዜ፣ ምንም ያልደከማቸው የላማናውያን ሠራዊቶች መጡባቸው፤ እናም አሰቃቂ ጦርነት አደረጉ፤ በዚህም የተነሳ ላማናው

፲፬ ᵐ ፫ ኔፊ ፲፪ ፣ ፴፩–፴፯።
፲፭ ᵃ ቅ.መ.መ. በቀል።
ለ ት.እና ቃ. ፹፪ ፣ ፹፫።
፲፯ ᵐ ፪ ኔፊ ፴ ፣ ፫–፳፡
፫ ኔፊ ፳፱ ፣ ፭።
፲፰ ᵐ ማቴ. ፲፱ ፣ ፳፰፤
ሉቃ. ፳፪ ፣ ፳፱–፴፣
ት.እና ቃ. ፳፱ ፣ ፲፪።
፲፱ ᵐ ፭ ኔፊ ፣ ፲፪ ፣ ፱–፲።
፳ ᵐ ት.እና ቃ. ፳፯ ፣ ፲፭።
ለ ቅ.መ.መ. ፍርድ፣
የመጨረሻው።
፳፩ ᵐ ት.እና ቃ. ፣ ፳።
ለ ቅ.መ.መ. አይሁዶች።
ሐ ፪ ኔፊ ፳፯ ፣ ፲፪፣
ሞዛያ ፯ ፣ ፳፯።
መ ፪ ኔፊ ፳፭ ፣ ፲፰።
፳፪ ᵐ አልማ ፳፱ ፣ ፭።

ያን የወደመችውን ከተማ ወሰዱ፣ እናም ብዙ ኔፋውያንን ገደሉና፣ ብዙ እስረኞች ንም ወሰዱ።

፫ እናም ቀሪዎቹ ሸሹና ከቴአንኩም ከተማ ነዋሪዎች ጋር ተቀላቀሉ። እንግዲህ የቴአን ኩም ከተማም በባሕሩ ዳርቻ ነበረች፤ እን ዲሁም ደግሞ በወደመችው ከተማ አጠ ገብ ነበረች።

፬ እናም የኔፋውያን ᵐወታደሮች ላማና ውያንን ለማጥቃት በመሔዳቸው መመ ታት ተጀመሩ፤ ይህ ባይሆን ኖሮ ላማናው ያን በእነርሱ ላይ ኃይል ሊኖራቸው አይ ችልም ነበርና።

፭ ነገር ግን እነሆ፣ የእግዚአብሔር ቅጣት በክፉዎች ላይ ይደርሳል፤ እናም ኃጥአን ᵐየሚቀጡት በኃጢአተኞች ነው፤ ምክን ያቱም ኃጥአን ናቸው የሰው ልጆችን ልብ ለደም መፋሰስ የሚቀሰቅሱትና።

፮ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን በቴአን ኩም ከተማ ላይ ጥቃት ለማካሄድ ዝግጅት አደረጉ።

፯ እናም እንዲህ ሆነ በሦስት መቶ ሥልሳ አራተኛው ዓመት ላማናውያን የቴአንኩ ምን ከተማ ይወስዱ ዘንድ ወደ ቴአንኩም ከተማ መጡ።

፰ እናም እንዲህ ሆነ በኔፋውያን ተሸ ነፉና ተገፍተው ተመለሱ። እናም ኔፋው ያን ላማናውያንን ማባረራቸውን በተመለ ከቱ ጊዜ በጥንካሬአቸው በድጋሚ ተኩ ራሩ፤ በጉልበታቸውም ተማምነው ወደ ፊት ቀጠሉና፣ በድጋሚ የወደመችውን ከተማ ወሰዱ።

፱ እናም እንግዲህ እነዚህ ነገሮች በሙሉ ተፈፅመዋል፣ እናም በኔፋውያንም ሆነ በላ ማናውያን በኩል በሺህ የሚቆጠሩ ተገደሉ።

፲ እናም እንዲህ ሆነ ሦስት መቶ ሥልሳ ስድስት ዓመት አለፈ፤ ላማናውያንም በድ ጋሚ ኔፋውያንን ለመውጋት መጡ፤ እናም ኔፋውያን ለሰሯቸው ክፉ ሥራዎች ንሰሃ ገና አልገቡም፤ ነገር ግን ያለማቋረጥ በክፋታ ቸው ቀጠሉ።

፲፩ እናም በኔፋውያን እንዲሁም በላማና ውያን መካከል አሰቃቂ የነበረውን ደም መፋሰስና ዕልቂት በአንደበት ለመግለፅም ሆነ ለሰው ሁኔታውን ሙሉ ለሙሉ ለመ ፃፍ በጣም አስቸጋሪ ነበር፤ እናም የሁሉም ልብ የጠጠረ ነበር ስለዚህ ያለማቋረጥ በሚ ፈሰው ደም ተደሰቱ።

፲፪ እናም በጌታ ቃል መሰረት፣ በእነዚህ ሰዎች መካከል እንደነበረው አይነት ታላቅ ᵐክፋት በሌሂም ልጆች ሆነ በእስራኤል ቤት ሁሉ መካከል በጭራሽ አልነበረም።

፲፫ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን የወደ መችውን ከተማ ወሰዱ፤ እናም ይህም የሆነ በት ምክንያት ᵐቁጥራቸው ከኔፋውያን ይበ ልጥ ስለነበር ነው።

፲፬ እናም ደግሞ ወደ ቴአንኩም ከተማ ዘመቱና፣ ነዋሪዎችዋን አስወጡ፣ እናም ከሴቶችና ልጆች በተጨማሪ ብዙ እስረኞ ችን ወሰዱ፣ እናም ለሚያመልኩት ᵐጣዖት መስዋዕት አቀረቡዋቸው።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ በሦስት መቶ ሥልሳ ሰባተኛው ዓመት፣ ኔፋውያን ላማናውያን ሴቶቻቸውንና ልጆቻቸውን መስዋዕት ስላ ደረጉባቸው ላማናውያንን በእጅጉ አጠቁአ ቸው፤ ስለዚህ በድጋሚ ላማናውያንን አሸ ነፉአቸውና ከምድራቸውም አባረሩአቸው።

፲፮ እናም እስከ ሦስት መቶ ሰባ አምስ ተኛው ዓመት ድረስ ላማናውያን በድጋሚ ኔፋውያንን አልወጉአቸውም።

፲፯ እናም በዚህ ዓመት ባላቸው ኃይል ሁሉ ኔፋውያንን ወጉአቸው፤ እናም በቁ ጥርም ብዙ በመሆናቸው አልተቆጠሩም ነበር።

፲፰ እናም ᵐከዚህ ጊዜም ጀምሮ ኔፋውያን በላማናውያን ላይ ድል አላገኙም፤ ነገር ግን ጨዛ በፀሀይ እንደሚበተን እነርሱም መጥ ፋት ጀመሩ።

፩ ፩ ሀ ሞር. ፫፡፲።
፪ ሀ ት.እና ቃ. ፳፫፡፴፫።
፲፪ ሀ ዘፍጥ. ፮፡፭፤
፫ ኔፊ ፱፡፱።
፲፫ ሀ ሞር. ፭፡፮።
፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. ጣአት አምላኪ።
፲፰ ሀ ሞር. ፫፡፫።

፲፱ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን የወ
ደመችውን ከተማ አጠቁ፤ እናም እጅግ
አሰቃቂ የሆነ ውጊያ በወደመችው ምድር
ነበር፣ በዚያም ኔፋውያንን አሸነፉአቸው።
፳ እናም በድጋሚ እነርሱ ከፊታቸው
ሸሹና፣ ወደ ቦአዝ ከተማም መጡ፤ እናም
በዚያም ላማናውያንን በድፍረት ተቋቋሙ፤
ስለዚህ ላማናውያንም በእነርሱ ላይ በድ
ጋሚ እስከሚመጡ ድረስ አላሸነፉአቸ
ውም ነበር።
፳፩ እናም ለሁለተኛ ጊዜ ወደ እነርሱ
በመጡ ጊዜ፣ ኔፋውያን ተባረሩና፣ በታ
ላቅ ሁኔታም ተገደሉ፤ ሴቶቻቸውና ልጆ
ቻቸው በድጋሚ ለጣዖት መስዋዕት ተደ
ረጉ።
፳፪ እናም እንዲህ ሆነ ኔፋውያን በድጋሚ
በከተማዋም ሆነ በየመንደሩ ያሉትን ነዋ
ሪዎቻቸውን በሙሉ ወስደው ከፊታቸው
ሸሹ።
፳፫ እናም እንግዲህ እኔ፣ ሞርሞን፣
ላማናውያን ምድሪቱን ለማጥፋት እንደተ
ቃረቡ በመገንዘቤ፤ ስለዚህ *ሀ*ወደሺም ኮረ
ብታ ሄድኩና፣ አማሮን ለጌታ የደበቀውን
መዛግብት በሙሉ ወሰድኩ።

ምዕራፍ ፭

*ሞርሞን የኔፊን ሠራዊት በድጋሚ የደም
መፋሰስና ዕልቂት ወዳለበት ውጊያ መራ
ቸው—መፅሐፈ ሞርሞን ኢየሱስ ክርስ
ቶስ መሆኑን ለእስራኤል ሁሉ ለማሳመን
ይመጣል—ላማናውያን ባለማመናቸው
ይበተናሉ፣ እናም መንፈስም ከእነርሱ
ጋር መሆኑን ያቆማል—በኋለኛው ቀን
ከአህዛብ ወንጌልን ይቀበላሉ። ከ፫፻፫፷፭–
፫፻፯፹፬ ዓ.ም. ገደማ።*

፩ እናም እንዲህ ሆነ ከኔፋውያን መካከል
ሔድኩና፣ እነርሱን ከእንግዲህ አልረዳቸ
ውም ብዬ ለገባሁት *ሀ*መሃላ ንሰሃ ገባሁ፤
እናም በድጋሚም በወታደሮቻቸው ላይ
ስልጣን ሰጡኝ ምክንያቱም እኔ ከስቃያ
ቸው ለማስለቀቅ የምችል አድርገው ይገ
ምቱ ስለነበር ነው።
፪ ነገር ግን እነሆ፣ *ሀ*ተስፋ አልነበረኝም፣
ምክንያቱም የጌታ ቅጣት በእነርሱ ላይ እን
ደሚመጣ አውቅ ነበርና፤ እነርሱ ስለኃጢ
አቶቻቸው ንሰሃ አልገቡምና፣ ነገር ግን ወደ
ፈጣሪያቸው ፀሎት ሳያደርጉ ለህይወታ
ቸው ይታገሉ ነበርና።
፫ እናም እንዲህ ሆነ ላማናውያን እኛ ወደ
ዮርዳኖስ ከተማ ስንሸሽ በእኛ ላይ መጡ
ብን፤ ነገር ግን እነሆ፣ ስለተሸነፉ በዚያን
ጊዜ ከተማዋን የራሳቸው አላደረጉም።
፬ እናም እንዲህ ሆነ በድጋሚ መጡብን፣
እኛም ከተማዋን ተቆጣጥረን ነበር። እናም
ደግሞ በኔፋውያን ተይዘው የነበሩ ሌሎች
ከተሞች፣ የምድራችንን ነዋሪዎች ለማ
ጥፋት ከእኛ በፊት የነበሩትን ስፍራዎች
ለመያዝ የማያስችሏቸው ጠንካራ ምሽጎች
ነበሩ።
፭ ነገር ግን እንዲህ ሆነ ባለፍንበት ምድር
ሁሉና፣ ያልተሰባሰቡት ነዋሪዎች በላማና
ውያን ጠፉ፣ እናም ከተሞቻቸውና መንደ
ሮቻቸው በእሳት ተቃጠሉ፤ እናም ሦስት
መቶ ሰባ ዘጠኝ ዓመት በዚህ አለፈ።
፮ እናም እንዲህ ሆነ በሦስት መቶ ሰማንያ
ኛው ዓመት፣ ላማናውያን በድጋሚ ሊዋጉን
መጡ፣ እኛም በድፍረት ተቋቋምናቸው፤
ነገር ግን ይህ ሁሉ ከንቱ ነበር፣ ምክንያቱም
በቁጥር እጅግ ብዙ ስለነበሩ የኔፋውያን ህዝ
ቦች በእግራቸው ሥር ረጋገጡአቸው።
፯ እናም እንዲህ ሆነ በድጋሚ ሸሽንና፣
ሸሽታቸው ከላማናውያን ፈጣን የነበሩት
አመለጡና፣ ከላማናውያን ሸሽተው ሊያ
መልጡ ያልቻሉት ተጠረጉና ጠፉ።
፰ እናም እንግዲህ እነሆ፣ እኔ ሞርሞን፣
የሰዎች ነፍስ በፊቴ እንደነበረው በዐይኔ
እንደተመለከትኩት አሰቃቂ የሆነ የደም
መፋሰስና ዕልቂት ዓይነት ስቃይ እንዲ
ጣል አልፈልግም፤ ነገር ግን እነዚህ ነገ

፳፫ *ሀ* ሞር. ፩፡ ፫።
፳፭ ፩ *ሀ* ሞር. ፫፡ ፲፩።
፪ *ሀ* ሞር. ፫፡ ፲፪።
፰ *ሀ* ሉቃ. ፲፪፡ ፪–፫፣
፪ ኔፊ ፳፯፡ ፲፩፣
ት. እና ቃ. ፩፡ ፫።

ሮች በእርግጥ እንዲታወቁ መደረጉንና፣ የተደበቁት ሁሉም ነገሮች በሰገነት ᵘመገ ለጥ እንዳለባቸው በማወቅ፣

፱ እናም ደግሞ የዚህ ህዝብ ቅሪት የሆኑ ትና ደግሞ ጌታ ᵛይበትኗቸዋል ብሎ የተ ናገራቸው፣ እናም ይህም ህዝብ በመካከ ላቸው ዋጋ እንደሌላቸው እንደሚቆረጡ ጌታ የተናገረባቸው አህዛብ እነዚህን ነገሮች ማወቅ ᵃእንዳለባቸው ስለማውቅ—ስለዚህ በተቀበልኩት ትዕዛዝ ምክንያትና፣ ደግሞ በዚህ ህዝብ ክፋትም ታላቅ ሀዘን እንዳይ ኖራቸው፣ ስላየኋቸው ነገሮች በሙሉ ለመ ፃፍ ባለመድፈሬ ᵇትንሽ ታሪክ አሳጥሬ እፅ ፋለሁ።

፲ እናም አሁን እነሆ፣ ይህን ለዘራቸውና፣ ደግሞ የእስራኤል ቤት ለሚንከባከቧቸውና በረከታቸውን ስለሚገነዘቡት እናም ከየት እንደሚመጣ ለሚያውቁትም አህዛብም እናገራለሁ።

፲፩ እንደነዚህ አይነቶች በእስራኤል ቤት መቅሰፍት እንደሚያዝኑ አውቃለሁና፤ አዎን፣ በዚህ ህዝብ መጥፋትም ያዝናሉ፤ ህዝቡም በኢየሱስ ተቀባይነትን ያገኙ ዘንድ ንሰሃ ባለመግባታቸውም ያዝናሉ።

፲፪ እንግዲህ ᵛእነዚህ ነገሮች የያዕቆብ ቤት ᵃቅሪት ለሆኑት የተፃፉ ናቸው፤ እናም በዚ ህም ስርዓት የተጻፈው ክፋት ወደእነርሱ ወደፊት እንደማያመጣቸው በእግዚአብ ሔር በመታወቁ ነው፤ እናም በራሱ ጊዜ ይገለጡ ዘንድ በጌታም ᵇተደብቀዋል።

፲፫ እናም ይህ እኔ የተቀበልኩት ትዕዛዝ ነው፤ እናም እነሆ ጌታ በጥበቡ ተስማሚ ነቱን በተመለከተ ጊዜ በጌታ ትዕዛዝ መሰ ረት ይመጣሉ።

፲፬ እናም እነሆ፣ ᵛከአይሁዶች መካከል ወደማያምኑት ይሄዳሉ፤ ለዚህ ዓላማም ይሄዳሉ—ኢየሱስ ክርስቶስ፣ የህያው እግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ᵃለማሳመን፤ አብም ᵇቃል ኪዳኑ ይፈፀም ዘንድ አይሁ ዶችን እንዲሁም የእስራኤል ቤት የሆኑትን በሙሉ ጌታ አምላካቸው ወደሰጣቸው ወደ ትውልድ ምድራቸው ለመመለስ ታላቅና ዘላለማዊ ዓላማውን በሚወደው በልጁ አማ ካይነት እንደሚያመጣ ለማሳመን፤

፲፭ እናም ደግሞ ᵛየዚህ ህዝብ ዘር የሆኑ ትም ከአህዛብ ᵃየሚሄድላቸውን ወንጌሉን ይበልጥ እንዲያምኑ ዘንድ፤ ምክንያቱም ይህ ህዝብ ᵇይበተናል፣ እናም ጨለማ፣ የጎ ደፈ፣ እናም ከመካከላችን ከነበረው ነገር በላይ፣ አዎን፣ በላማናውያን መካከል ከነ በረው የበለጠ ለመግለፅ በማያስችል ሁኔታ የሚያስጠሉ ᶜይሆናሉና፤ እናም ይህም የሆነው ባለማመናቸውና ጣዖት አምላኪ በመሆናቸው ነው።

፲፮ እነሆም፣ የጌታ መንፈስ ከአባቶቻቸው ጋር ᵛመስራቱን አቁሟል፤ እናም በዓለም ውስጥ ያለክርስቶስና ያለእግዚአብሔር ናቸውና፤ እናም ᵃገለባ በነፋስ ፊት እንደ ሚሆነው ይበተናሉና።

፲፯ በአንድ ወቅት አስደሳች ሰዎች ነበሩ፣ እንዲሁም ክርስቶስም ᵛእረኛቸው ነበር፤ አዎን፣ በእግዚአብሔር አብም እንኳን ተመርተው ነበር።

፲፰ ነገር ግን አሁንም እነሆ፣ ገለባ በነፋስ ፊት እንደሚወሰደው ወይም ሸራ እናም መሃለቁ ሳይኖራት ወይም ቀጽዘፊም እን ደሌሉባት በሞገድ እንደምትናወጥ ጀልባ እነርሱም በሰይጣን ᵛተመርተዋል፤ እናም እርሷም እንደዚህ እንደሆነች፣ እነርሱም ናቸው።

፱ ᵛ ፫ ኔፊ ፲፯፡፳፡
ᵃ ፬ ኔፊ ፩፡ ፵፱።
ᵇ ሞር. ፩፡ ፩።
፲፡ ᵛ ኢኖስ ፩፡ ፲፯፡
ሔሌ. ፲፭፡ ፲፩–፲፫።
ቅ.መ.መ. መፅሐፈ ሞርሞን።
ᵃ ት.እና ቃ. ፫፡ ፲፯–፳።
ᵇ ሞር. ፰፡ ፱፡ ፲፫–፲፬፡
ᶜ ሞሮኒ ፲፡ ፩–፪።
፲፡ ᵛ ፪ ኔፊ ፳፱፡ ፲፫፡ ፴፡ ፯–፰።
ቅ.መ.መ. አይሁዶች።
ᵃ ፪ ኔፊ ፳፭፡ ፲፯–፲፯።
ᵇ ፫ ኔፊ ፳፱፡ ፩–፫።
፲፫ ᵛ ፫ ኔፊ ፳፩፡ ፫–፯፡ ፳፡ ፳–፳፯።
ᵃ ፩ ኔፊ ፲፫፡ ፳–፳፱፡ ፴፰፡
ሞር. ፯፡ ፰–፱።
ᵃ ፩ ኔፊ ፲፡ ፲፪–፲፬፡
፫ ኔፊ ፲፯፡ ፰።
መ ፪ ኔፊ ፳፯፡ ፴፫።
፲፯ ᵛ ዘፍጥ. ፮፡ ፫፡
ኤተር ፪፡ ፲፭።
ᵃ መዝ. ፩፡ ፬።
፲፯ ᵛ ቅ.መ.መ. መልካሙ እረኛ።
፲፰ ᵛ ፪ ኔፊ ፳፰፡ ፳፩።

፲፤ እናም እነሆ፣ ጌታም በምድሪቷ ለመ
ቀበል የሚችሉትን በረከት አስቀምጦላቸ
ዋል፣ ᵐአህዛብም ምድሪቱን ይዘዋታልና።
፲፩ ነገር ግን እነሆ፣ እነርሱም በአህዛብ ይባ
ረራሉና ይበተናሉ፤ እናም በአህዛብ ከተባ
ረሩና ከተበተኑ በኋላ፣ እነሆ፣ ጌታ ከአብ
ርሃም እንዲሁም ከእስራኤል ቤት በሙሉ
ጋር የገባውን ᵐቃል ኪዳን ᵃያስታውሳል።
፲፪ እናም ደግሞ ጌታ በፊቱ ለእነርሱ የተ
ቀመጠለትን የፃድቃኖች ᵐፀሎት ያስታው
ሳል።
፲፫ እና እንግዲህ አህዛብ ሆይ፣ ንሰሃ ካል
ገባችሁና ክፉ ስራችሁን ካልተዋችሁ በቀር
በእግዚአብሔር ኃይል በፊቱ እንዴት ለመ
ቆም ትችላላችሁ?
፲፬ በእግዚአብሔር እጅ መሆናችሁን
አታውቁምን? ስልጣን ሁሉ የእርሱ መሆ
ኑንና በታላቅ ᵐትዕዛዙም ምድር በአንድነት
እንደ መጽሐፍ ጥቅልል ᵃየምትጠቀለል
መሆኗን አታውቁምን?
፲፭ ስለዚህ፣ እናንተ ንሰሃ ግቡ፣ እናም
በፊቱም ራሳችሁን አዋርዱ፣ ያለበለዚያ
ፍርዱ በላያችሁ እንዳይመጣባችሁ—ያለ
በለዚያ የያዕቆብ ዘር ቅሪት የሆኑት በመካከላ
ችሁ ᵐእንደአንበሳ ይመጣሉ፣ እናም ይበጫ
ጭቋቸኋልና፣ ሊያድን የሚችል አይኖርም።

ምዕራፍ ፮

*ኔፋውያን ለመጨረሻው ውጊያ በከምራ
ምድር ተሰባሰቡ—ሞርሞን በከምራ ኮረ
ብታ ቅዱስ የሆኑትን መዛግብት ደበቃ
ቸው—ላማናውያን ድል አደረጉ፣ እናም
የኔፋውያንም ሀገር ጠፉች—በመቶ
ሺህ የሚቆጠሩ በጎራዴ ተገደሉ።
በ፫፻፸፯ ዓ.ም. ገደማ።*

፩ እናም እንግዲህ የህዝቦቼ የኔፋውያንን
ᵐጥፋት በተመለከተ ታሪኬን እጨርሳለሁ።
እናም እንዲህ ሆነ ከላማናውያን ፊት ዘመ
ትን።
፪ እናም እኔ ሞርሞን፣ ለላማናዊው ንጉስ
ደብዳቤ ፃፍኩና፣ ከሞራ ተብሎ በሚጠ
ራው ኮረብታ አካባቢ በከሞራ ᵐምድር
ህዝባችንን እንድንሰበስብ እንዲፈቀድል
ንና ከእነርሱ ጋር ለመዋጋት እንድንችል
መፈለጌን ጠየቅሁ።
፫ እናም እንዲህ ሆነ የላማናውያን ንጉስ
እንደፈለግሁትም ፈቀደልኝ።
፬ እናም እንዲህ ሆነ ወደ ከሞራ ምድር
ሄድንና፣ በከሞራ ኮረብታ ዙሪያ ድንኳ
ናችንን ተከልን፤ እናም ምድሪቱም ብዙ
ውሀዎች፣ ወንዞችና፣ ምንጮች ነበሩባት፤
እናም እዚህ በላማናውያን ላይ ብልጫ እን
ደምንይዝ ተስፋ አደረግን።
፭ እናም ሦስት መቶ ሰማንያ አራት ዓመ
ታት በአለፈ ጊዜ፣ የተቀሩትን ህዝቦቻችንን
በከሞራ ምድር ሰበሰብን።
፮ እናም እንዲህ ሆነ ህዝባችንን በሙሉ
በአንድነት በከሞራ ምድር በሰበሰብን
ጊዜ፣ እነሆ እኔ ሞርሞን፣ ማርጀት ጀመ
ርኩ፤ የሕዝቤም የመጨረሻው ትግል መሆ
ኑን በማወቄና፣ በአባቶቻችን የተረከብነ
ውን ቅዱስ የሆነ መዝገብ በላማናውያን እጅ
እንዳይገባ በጌታ በመታዘዜ (ምክንያቱም
ላማናውያን ያጠፏቸዋልና) ስለዚህ ᵐይህን
መዝገብ ከኔፊ ሰሌዳ ላይ ፃፍኩት፣ እናም
ለልጄ ᵃለሞሮኒ ከሰጠኋቸው ᵃከእነዚህ ትን
ንሾች ሠሌዳዎች በቀር በጌታ የተሰጠኝን
መዛግብት በሙሉ በከሞራ ኮረብታ ውስጥ
መደበቅኋቸው።
፯ እናም እንግዲህ ህዝቦቼ ከነሚስቶቻ
ቸውና፣ ከነልጆቻቸው፣ አሁን የላማናው

፲፤ ᴴ ፫ ኔፊ ፯፡፲፮–፳፡፡
፲፩ ᴴ ቅ.መ.መ. የአብርሐም
ቃል ኪዳን።
ᵃ ፫ ኔፊ ፲፯፡፳–፲፪።
፲፭ ᴴ ኢኖስ ፩፡፲፪–፲፡፤
ሞር. ፱፡፴፯–፴፯።
፲፫ ᴴ ሔለ. ፲፪፡፳–፲፯።

ᵃ ፫ ኔፊ ፲፯፡፣ ፫፡
፲፭ ᴴ ሚክ. ፭፡፰፤
፫ ኔፊ ፳፡፲፭–፲፯።
፮ ፭ ᴴ ፩ ኔፊ ፲፪፡፲፤
ጄረም ፩፡፲፣
አልማ ፴፭፡፱–፲፡
ሔለ. ፲፫፡፭–፲፩።

፪ ᴴ ኤተር ፱፡፫።
፮ ᴴ ቅ.መ.መ. ሰሌዳዎች።
ᵃ ሞር. ፰፡፩።
ᵐ ኤተር ፲፭፡፲፩።

ያን [a]ወታደሮች ወደ እነርሱ ሲዘምቱ ተመ
ለከቱ፤ እናም የክፉዎችን ሁሉ ደረት በሚ
ሞላው አሰቃቂ ሞት ፍርሀት እነርሱን ለመ
ቀበል ይጠባበቁ ነበር።
፰ እናም እንዲህ ሆነ እነርሱ እኛን ለመ
ውጋት መጡና፣ በቁጥር ብዙ ስለነበሩ እያ
ንዳንዱ ነፍስ በፍርሃት ተሞልታ ነበር።
፱ እናም እንዲህ ሆነ ህዝቤንም በጎራዴና፣
በደጋን፣ እናም በቀስትና፣ በምሳር፣ እን
ዲሁም በሁሉም ዓይነት የጦር መሳሪያዎች
አጠቁአቸው።
፲ እናም እንዲህ ሆነ ሰዎቻችን ተገደሉ፤
አዎን፣ ከእኔ ጋር የነበሩት አስር ሺዎች
ሳይቀሩ ተገደሉ፤ እኔ ቆስዬ በመካከላቸው
ወደቅሁ፤ እናም በአጠገቤ አለፉና፣ አል
ገደሉኝም።
፲፩ እናም በመካከላችን ሄዱና ከሃያ አራ
ታችን በስተቀር (ከመካከላቸውም ልጄ
ሞሮኒ ነበር) [b]ሁሉንም ህዝቦቼን ገደሉና
እኛ ከሞቱት ህዝቦቻችን በመትረፋችን፣
ላማናውያን ወደ ጦር ሰፍራቸው ሲመለሱ፣
በነጋታው ከከሞራ ኮረብታ ጫፍ ላይ እኔ
በፊታቸው ሆኜ እመራቸው የነበሩትን የተ
ገደሉትን አስር ሺህ ህዝቦቼን ተመለከትን።
፲፪ እናም ደግሞ በልጄ ሞሮኒ ይመሩ የነ
በሩ አስር ሺህ የሚሆኑ ህዝቦቼን ተመለከ
ትናቸው።
፲፫ እናም እነሆ አስር ሺህ የሚሆኑ
የጊድጊዶና ሰዎች ወድቀዋል፣ እናም እር
ሱም ደግሞ በመካከላቸው ነበር።
፲፬ እናም ላማም ከአስር ሺዎቹ ጋር ወድ
ቋል፤ ጊልጋልም ከአስር ሺዎቹ ጋር ወድ
ቋል፤ እናም ሊምሀም ከአስር ሺዎቹ ጋር
ወድቋል፤ ዬኔዩም ከአስር ሺዎች ጋር ወድ
ቋል፤ እናም ቁሜኒሀምና፣ ሞሮኒሃም፣
አንቲዩነምና፣ ሺብሎም፣ እናም ሼምና፣
ጆሹ፣ እያንዳንዳቸው ከአስር ሺዎቻቸው
ጋር ወደቁ።
፲፭ እናም እንዲህ ሆነ ከእያንዳንዳቸው
አስር ሺዎች ጋር በጎራዴ የተገደሉ አስር
መሪዎች ነበሩ፤ አዎን፣ ከእኔ ጋር ከነበ
ሩት ከሃያ አራቱ፣ እናም ደግሞ በሃገሪቱ
በስተደቡብ ካመለጡት ጥቂቶችና፣ ወደ
ላማናውያን ከከዱት ጥቂቶች በስተቀር፣
[c]ሁሉም ህዝቦቼ ወድቀዋል፤ እናም ሥጋቸ
ውና፣ አጥንታቸው፣ እንዲሁም ደማቸው
በምድረ ገፅ ላይ ሆኖ፣ በምድሪቱ ላይ እን
ዲበሰብሱና፣ እንዲበላሹ እናም ወደ እናት
ምድርም እንዲመለሱ በገዳዮቻቸው እጅ
ተተዉ።
፲፮ እናም ነፍሴ ሕዝቤ በመገደሉ በጭን
ቀት ተከፈለች፣ እናም እንዲህ ስል
ጮኽኩ፥
፲፯ እናንተ መልከ መልካሞች ሆይ፣
ከጌታ መንገድ እንዴት ልትለዩ ቻላችሁ!
እናንተ መልከ መልካሞች ሆይ፣ እናንተን
ለመቀበል ክንዶቹን ዘርግቶ የቆመውን ኢየ
ሱስን እንዴት ልትቃወሙት ቻላችሁ!
፲፰ እነሆ፣ ይህንን ባታደርጉ ኖሮ፣ አትወ
ድቁም ነበር። ነገር ግን እነሆ፣ ወድቃችኋል
እናም ስለሞታችሁ እተክዛለሁ።
፲፱ እናንተ መልከ መልካም ወንዶችና
ሴት ልጆች ሆይ፤ አባቶችና እናቶች ሆይ፣
እናም ባሎችና ሚስቶች ሆይ፤ እናንተ
መልከ መልካም የሆናችሁ፣ እንዴት ልት
ወድቁ ቻላችሁ!
፳ ነገር ግን እነሆ፣ እናንተ ጠፍታች
ኋል፣ እናም የእኔ ሀዘን እናንተን ሊመል
ሳችሁ አይችልም።
፳፩ እናም ሟች የሆነው ሰውነታችሁ
በቅርቡ ህያው የሚሆንበት ቀን ይመጣል፤
እናም ይህ ሰውነት ዛሬ የሚበሰብስ የሆ
ነው በቅርቡ [d]የማይበሰብስ ሰውነት በመ
ሆን ይለወጣል፤ እናም በስራችሁ መሰረት
ሊፈረድባችሁ በክርስቶስ የፍርድ ወንበር
ፊት መቆም ይኖርባችኋል፤ እናም እናንተ
ፃድቅ ብትሆኑ፣ ከዚያም ከእናንተ በፊት
ካለፉት አባቶቻችሁም ጋር የተባረካችሁ
ትሆናላችሁ።
፳፪ አቤቱ ከዚህ ታላቅ ጥፋት በፊት

፯ሀ ፩ ኔፊ ፲፪፥ ፲፭።
፲፩ሀ ፩ ኔፊ ፲፪፥ ፲፱–፳፤
ሔለ. ፲፭፥ ፲፯።
፲፭ሀ አልማ ፱፥ ፳፬።
፳፩ሀ ፩ ቆሮ. ፲፭፥ ፶፫–፶፬።

ንሰሃ በገባችሁ ኖሮ። ነገር ግን እነሆ፣ እና ንተ አልፋችኋል፣ እናም አብ፣ አዎን ዘለ አለማዊው የሰማይ አባት የእናንተን ሁኔታ ያውቃል፤ እናም እርሱም እንደ ᵐፍርዱና ᵃምህረቱ ያደርግላችኋል።

ምዕራፍ ፯

ሞርሞን የኋለኛው ዘመን ላማናውያን በክርስቶስ እንዲያምኑ፤ ወንጌሉን እን ዲቀበሉ እናም እንዲድኑ አጥብቆ ጋበዛ ቸው—መጽሐፍ ቅዱስን የሚያምኑ ሁሉ መፅሐፈ ሞርሞንን እንዲሁ ያምናሉ። በ፲፱፻፵፰ ዓ.ም. ገደማ።

፩ እናም አሁን፣ እነሆ፣ የአባቶቻቸውን ነገሮች ያውቁ ዘንድ እግዚአብሔር ቃሌን ከሰጣቸው፣ ለነዚህ ለተረፉት የዚህ ሕዝብ ᵐቅሪት ለሆኑት ጥቂት እናገራለሁ፤ አዎን፣ የእስራኤል ቤት ቅሪት ለሆናችሁ ለእናንተ እናገራለሁ፤ እናም የምናገራቸው ቃላት እነዚህ ናቸው፥

፪ እናንተ ᵐከእስራኤል ቤት መሆናችሁን እወቁ።

፫ ንሰሃ መግባት እንዳለባችሁ፣ አለበለዚያ ለመዳን እንደማትችሉ እወቁ።

፬ የጦር መሳሪያዎቻችሁን መጣል እንዳ ለባችሁ እወቁ፣ እናም ከእንግዲህ በደም መፍሰስ በምንም አትደሰቱ፣ እናም ከእን ግዲህ እግዚአብሔር ካላዘዛችሁ በስተቀር የጦር መሳሪያዎቻችሁን በድጋሚ አታንሱ።

፭ አባቶቻችሁ ያወቁትን ᵐለማወቅና፣ እናም ለኃጢአቶቻችሁ ሁሉና ለክፋቶቻ ችሁ ንሰሃ መግባት እንዳለባችሁ፣ እናም በአይሁዶች የተገደለው ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑንና፣ እርሱም በአብ ኃይል ዳግም እንደተነሳ፣ ስለዚህ በመቃብር ላይ ᵃድል እንዳደረገ ᵃማመን እንዳለባችሁ እወቁ፣ እናም ደግሞ በእር ሱም የሞት መውጊያ ተውጣለች።

፮ እናም እርሱም ሰውም ᵐበፍርድ ወን በር ፊት ለመቆም የሚነሳበትን የሙታንን ᵃትንሣኤ ያመጣል።

፯ እናም በእርሱም ፊት በፍርድ ቀን ᵐጥፋተኛ ሳይሆን የሚገኝ፣ ᵃአንድ አም ላክ የሆኑትን፣ አብ፣ እናም ወልድ፣ እናም መንፈስ ቅዱስን መጨረሻ በሌለው ᵃደስታ ያለማቋረጥ ከበላይ ᵐዘማሪዎች ጋር ለማወ ደስ በእግዚአብሔር መንግስት በፊቱ ᵐእን ዲኖር የሚሰጥበትን ለዓለም ᶜቤዛነትን አም ጥቷል።

፰ ስለዚህ ንሰሃ ግቡና፣ በኢየሱስ ስም ተጠመቁ፣ እናም በዚህ መዝገብ ብቻ ሳይ ሆን ነገር ግን ᵐከአይሁዶች ለአህዛብ የሚ መጣውን ᵃመዝገብ ውስጥ የተመሰረተውን የክርስቶስን ᵃወንጌል በጥብቅ ያዙ፣ ይህም መዝገብ ከአህዛብ ᵐለእናንተ ይመጣል።

፱ እነሆም፣ ይህም እናንተ ᵐእንድታምኑ በት ነው ᵃየተፃፈው፤ እናም ያንን የም ታምኑት ከሆነ፣ ይህንንም ደግሞ ታምናላ ችሁ፤ እናም ይህንን የምታምኑ ከሆነ ስለአ ባቶቻችሁና፣ ደግሞ በእግዚአብሔር አማ ካኝነት በመካከላቸው የተሰራውን ድንቅ ሥራዎች ጭምር ታውቃላችሁ።

፲ እናም ደግሞ የያዕቆብ ዘር ቅሪት መሆ ናችሁን ታውቃላችሁ፤ ስለዚህ ከመጀመ ሪያዎቹ የቃል ኪዳን ህዝቦች ጋር ተቆጥራ ችኋል፣ እናም በክርስቶስ የምታምኑ ከሆነ፣ እናም እርሱ በሰጠው ትእዛዝ መሰረት፣

፰ ፪ ሀ ቅ.መ.መ. ፍትህ።
ለ ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።
፯ ፩ ሀ ሐሌ. ፲፯ ፡ ፲፩–፲፫።
፪ ሀ አልማ ፲ ፡ ፫።
፩ ሀ ፪ ኔፊ ፫ ፡ ፲፪።
ለ ኢሳ. ፳፭ ፡ ፳፡
ሞዛያ ፲፭ ፡ ፯–፳።
ሐ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
፮ ሀ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—ዳኛ፤ ፍርድ፣ የመጨረሻው።
ለ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
፯ ሀ ቅ.መ.መ. ማፅደቅ፣ ከበደል ነጻ መሆን።
ለ ት. እና ቃ. ፳ ፡ ፳፰።
ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ።
ሐ ቅ.መ.መ. ደስታ።
መ ሞዛያ ፪ ፡ ፳፰።
ሠ ፩ ኔፊ ፲ ፡ ፳፩፤ ት. እና ቃ. ፫፯ ፡ ፳፪፤ ሙሴ ፮ ፡ ፶፯።
ረ ቅ.መ.መ. ቤዛ፣ ማዳን፣ ቤዛነት።
፰ ሀ ፪ ኔፊ ፳፱ ፡ ፬–፲፫።
ለ ቅ.መ.መ. መፅሐፍ ቅዱስ።
ሐ ቅ.መ.መ. ወንጌል።
መ ፩ ኔፊ ፲፫ ፡ ፴፰።
፱ ሀ ፩ ኔፊ ፲፫ ፡ ፴፰–፴፩።
ለ ቅ.መ.መ. መፅሐፈ ሞርሞን።

የአዳኛችንን ᵐምሳሌ በመከተል መጀመሪያ በውኃ በኋላም በእሳትና በመንፈስ ቅዱስ የምትጠመቁ ከሆነ በፍርድ ቀን ለእናንተ መልካም ይሆንላችኋል። አሜን።

ምዕራፍ ፰

ላማናውያን ኔፋውያንን አሳደዱአቸውና አጠፉአቸው — መፅሐፈ ሞርሞን በእግዚ አብሔር ኃይል ይመጣል — ቁጣን ለሚና ገሩ እናም ከጌታ ሥራ ጋር ለሚጣሉ ዋይታ ታውጀባቸዋል — የኔፋውያን መዛግብት በኃጢያት፣ በክፋትና በክህደት ዘመን ይመጣል። ከ፬፻ – ፬፻ሯ፬ ዓ. ም. ገደማ።

፩ እነሆ እኔ ᵐሞሮኒ፣ የአባቴ የሞርሞንን ᵃታሪክ እፈፅማለሁ። እነሆ፣ የምፅፋቸው ጥቂት ነገሮች ብቻ ነው ያሉኝ፣ እነዚህም ነገሮች አባቴ ያዘዘኝ ናቸው።

፪ እናም እንግዲህ እንዲህ ሆነ በከሞራ ከነበረው ᵐታላቅና ከፍተኛ ጦርነት በኋላ፣ እነሆ፣ በሃገሪቱ በስተደቡብ በኩል የሸሹት ኔፋውያን ሁሉም እስከሚጠፉ ድረስ ᵃበላ ማናውያን ታድነው ነበር።

፫ እናም አባቴ ደግሞ በእነርሱ ተገደ ለና፣ የሕዝቤን አሳዛኝ የሆነ ታሪክ ለመጻፍ እንኳ ᵐብቻዬን ቀረሁ። ነገር ግን፣ እነሆ እነ ርሱ አልፈዋል፣ እናም እኔ የአባቴን ትዕ ዛዝ እፈፅማለሁ። እናም ይግደሉኝ አይ ግደሉኝ፣ ምንም አላውቅም።

፬ ስለዚህ እፅፋለሁ እናም መዛግብቱን በመሬት ውስጥ እደብቃለሁ፤ እናም የትም መሄዴ አስፈላጊ አይደለም።

፭ እነሆ፣ አባቴ ᵐይህን ታሪክ ፅፏል፣ ዓላ ማውንም ፅፏል። እናም እነሆ፣ ᵃበሰሌዳ ዎቹ ላይ ቦታ ካገኘሁ እኔም እፅፈዋለሁ፣ ነገር ግን ቦታ አላገኘሁም፤ የብረት አፈርም የለኝም፣ ምክንያቱም ብቻዬን ነኝና። አባ ቴና ዘመዶቼ ሁሉ በጦርነት ተገድለዋል፤ እናም ወዳጆችም ሆኑ የምሄድበት የለኝም፤ እናም ጌታ ምን ያህል በህይወት እንድቆይ እንደሚፈቅድልኝ አላውቅም።

፮ እነሆ፣ ጌታችን እናም አዳኛችን ወደ ምድር ከመጣ ᵐአራት መቶ ዓመታት አል ፈዋል።

፯ እናም እነሆ ላማናውያን ሕዝቦቼን ኔፋ ውያንን በሙሉ እስከሚሞቱ ድረስ ከከ ተማ ከተማ እንዲሁም ከቦታ ቦታ አባረ ሩአቸው፤ እናም ᵐውድቀታቸውም ታላቅ ነበር፤ አዎን፣ የህዝቤ የኔፋውያን ጥፋት ታላቅና የሚያስገርም ነበር።

፰ እናም እነሆ፣ ይህንን ያደረገው የጌታ እጅ ነው። እናም ደግሞ እነሆ፣ ላማናው ያን እርስ በርሳቸው ᵐበጦርነት ላይ ናቸው፤ እናም ምድሪቱ በሙሉ የማያቋርጥ ግድያና ደም መፋሰስ ነበረባት፤ እናም ማንም የጦ ርነቱን ፍፃሜ አያውቅም።

፱ እናም አሁን፣ እነሆ፣ ከላማናውያንና በምድሪቱ ላይ ይኖሩ ከነበሩት ᵐሌቦች በስ ተቀር ማንም ባለመኖሩ ስለእነርሱ ከዚህ በላይ የምለው የለኝም።

፲ እናም የሰዎቹ ክፋትም ታላቅ በመሆኑ ጌታ በህዝቡ መካከል ᵐእንዲቀሩ እስካል ፈቀደላቸው ጊዜ ድረስ በምድሪቱ ከቀሩት ከኢየሱስ ᵃደቀመዛሙርት በቀር እውነተ ኛውን እግዚአብሔር የሚያውቅ ማንም የለም፤ እናም በምድር ገፅ ላይ የት መሆና ቸውንም ማንም ሰው አያውቅም።

፲፩ ነገር ግን እነሆ፣ ᵐአባቴና እኔ ተመል ክተናቸዋል፣ እናም እነርሱም እኛን አገ ልግለውናል።

፲፪ እናም ይህንን መዝገብ አግኝቶ ውስጡ ባሉት ጉድለቶች ምክንያት ያልኮነነው

፲ ሀ ፪ ኔፊ ፴፩፡ ፭–፱።
፰ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. ሞሮኒ፣ የሞርሞን ልጅ።
ለ ቅ.መ.መ. ሰሌዳዎች።
፪ ሀ ሞር. ፮፡ ፪–፲፭።
ለ ት.እና ቃ. ፫፡ ፲፰።
፫ ሀ ሞሮኒ ፱፡ ፳፪።
፭ ሀ ሞር. ፪፡ ፲፯–፲፰።
ለ ሞር. ፮፡ ፮።
፮ ሀ አልማ ፴፭፡ ፲።
፯ ሀ ፩ ኔፊ ፲፪፡ ፪–፫።
፰ ሀ ፩ ኔፊ ፲፪፡ ፳–፳፫።
፱ ሀ ሞር. ፪፡ ፰።
፲ ሀ ሞር. ፩፡ ፲፯።
፲፩ ሀ ፫ ኔፊ ፳፰፡ ፯፣ ኤተር ፲፪፡ ፲፯። ቅ.መ.መ. ሶስቱ ኔፋውያን ደቀ መዛሙርቶች።
፲፪ ሀ ፫ ኔፊ ፳፰፡ ፳፱–፳፮።

ከዚህ የበለጠ [ሀ]ታላቅ የሆኑ ነገሮችን ያውቃል። እነሆ፣ እኔ ሞሮኒ ነኝ፤ እናም የሚቻል ቢሆን ኖሮ ሁሉንም ነገር እንድታውቁ አደርጋለሁ።

፲፫ እነሆ፣ ይህንን ሕዝብ በተመለከተ ንግግሬን አቆማለሁ። እኔ የሞርሞን ልጅ ነኝ፣ እናም አባቴም የኔፊ [ሀ]ዘር ነበር።

፲፬ እናም ለጌታ ስል ይህንን መዝገብ [ሀ]የደበቅሁት እኔ ነኝ፤ በጌታ ትዕዛዝም የተነሳ ሰሌዳዎቹ ዋጋ የላቸውም። ምክንያቱም እርሱ በእውነት ማንም ቢሆን [ለ]ጥቅም ያገኝበት ዘንድ አይቀበለውም ብሏልና፤ ነገር ግን መዛግብቱ ታላቅ ዋጋ አላቸው፤ እናም እንዲታወቁ የሚያደርጋቸው ቢኖር ጌታ እርሱን ይባርከዋል።

፲፭ በእግዚአብሔር ካልተሰጠው በስተቀር ማንም ወደ ብርሃን ሊያወጣቸው ኃይል ሊኖረው አይችልም፤ ምክንያቱም በእግዚአብሔር ለክብሩ [ሀ]በቀናነት ይደረግ ዘንድ ወይንም ለጥንቱና ለረጅም ጊዜ ለተበተኑት የጌታ የቃል ኪዳን ልጆች ደህንነት እንዲሆን ፈቃዱ ነውና።

፲፮ እናም ይህ ነገር ወደ ብርሃን እንዲመጣ የሚያደርግ [ሀ]እርሱ የተባረከ ነው፤ በእግዚአብሔር ቃልም መሰረት ከጨለማው ወደ ብርሃን [ለ]ይመጣልና፤ አዎን ይህም ከምድር ይወጣል፣ እናም በጨለማው ውስጥም ሆኖ ያበራል፣ በሕዝቡም ይታወቃል፣ ይህም በእግዚአብሔር ኃይል ይደረጋል።

፲፯ እናም ስህተት ቢኖር እነርሱም የሰው ልጆች [ሀ]ስህተት ናቸው። ነገር ግን እነሆ፣ እኛ ምንም አይነት ስህተት አናውቅም፤ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ያውቃል፤ ስለዚህ፣ [ለ]የሚያስኮንነው ቢኖር በሲኦል እሳት አደጋ ላይ እንዳይሆን ይጠንቀቅ።

፲፰ እናም አሳዩኝ አለበለዚያ ትመታላችሁ ብሎ ለሚናገር—በጌታ የተከለከለውን እርሱ እያዘዘ መሆኑንም ይጠንቀቅ።

፲፱ እነሆም፣ በፍጥነት የሚፈርድ በእርሱም ላይ እንደዚሁ በፍጥነት [ሀ]ይፈረድበታል፤ ምክንያቱም ደመወዙም እንደስራው ይሆናልና፤ ስለዚህ፣ የሚማታ እርሱ በድጋሚ በጌታ ይመታል።

፳ ቅዱሳን መጽሐፍት የሚሉትን ተመልከቱ—ሰው አይምታ፣ ወይም አይፍረድ፤ ፍርድ የእኔ ናትና ይላል ጌታ፣ እናም ደግሞ በቀልም የእኔ ናት እናም እኔ እከፍለዋለሁ።

፳፩ እናም በጌታ ሥራ ላይና፣ የእስራኤል ቤት በሆኑት በጌታ የቃል ኪዳን ሕዝብ ላይ በቁጣ የሚናገርና ፀብን የሚያነሳ፣ እናም የጌታን ሥራ እናጠፋለን፣ ጌታም ከእስራኤል ቤት ጋር የገባውን ቃል ኪዳን አያስታውስም—በማለት የሚናገረው እርሱ ለመቆረጥና በእሳት ላይ ለመጣል አደጋ ላይ ነው፤

፳፪ ምክንያቱም የጌታ ቃል ኪዳን በሙሉ እስከሚፈፀም ድረስ ዘለዓለማዊው [ሀ]ዓላማው ይቀጥላል።

፳፫ [ሀ]የኢሳይያስን ትንቢት መርምሩ። እነሆ፣ እኔ ልፅፉቸው አልችልም። አዎን፣ እነሆ እንዲህ እላችኋለሁ፣ ከእኔ በፊት የነበሩት ይህችን ምድር ወርሰው የነበሩት ቅዱሳን [ለ]ይጮኻሉ፣ አዎን፣ ከትቢያውም እንኳን ቢሆን ወደ ጌታ ይጮኻሉ፤ እናም ጌታ ህያው እንደሆነ ከእነርሱ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን ያስታውሳል።

፳፬ እናም [ሀ]ፀሎታቸውም ስለወንድሞቻቸውም እንደሆነ ያውቃል። እናም እምነታቸውን ያውቃል፣ ምክንያቱም በስሙ

፲፪ ሀ ፫ ኔፊ ፳፮፥ ፮–፲፩።
፲፫ ሀ ፫ ኔፊ ፭፥ ፳።
፲፬ ሀ ሞሮኒ ፲፥ ፩–፪።
ለ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥ ፵፮።
፲፭ ሀ ት. እና ቃ. ፬፥ ፭።
፲፮ ሀ ፪ ኔፊ ፫፥ ፮–፯፣ ፲፩፣ ፲፫–፲፭።
ለ ኢሳ. ፳፱፥ ፲፰፤
፪ ኔፊ ፳፯፥ ፳፱።
፲፯ ሀ ሞር. ፱፥ ፴፩፣ ፴፫፤
ኤተር ፲፪፥ ፳፫–፳፰።
ለ ፫ ኔፊ ፳፱፥ ፭፤
ኤተር ፬፥ ፰።
፲፱ ሀ ጆ.ስ.ት. ማቴ. ፯፥ ፩–፪
(ተጨማሪ)፤
፫ ኔፊ ፲፬፥ ፩–፪፤
ሞሮኒ ፯፥ ፲፬።
፳፪ ሀ ት. እና ቃ. ፫፥ ፫።
፳፫ ሀ ፫ ኔፊ ፳፥ ፲፩፤
፳፫፥ ፩።
ለ ኢሳ. ፳፱፥ ፬፤
፪ ኔፊ ፫፥ ፲፱–፳፤
፳፮፥ ፲፮።
፳፬ ሀ ኢኖስ ፩፥ ፲፪–፲፰፤
ሞር. ፱፥ ፴፮፤
ት. እና ቃ. ፲፥ ፵፮።

[ለ]ተራሮችን ማንቀሳቀስ ይችላሉና፤ እናም በስሙም ምድርን ማናወጥ ይቻላቸዋልና፤ እናም በቃሉ ኃይልም [ሐ]ወህኒዎችም ወደ ምድር እንዲፈርሱ አድርጓል፤ አዎን፣ የጋለው ምድጃ እንኳ ሊጎዳቸው አልተቻለውም፤ የዱር አራዊትም ሆኑ መርዛማም እባቦች በቃሉ ኃይል ሊጎዱቸው አልቻሉም።

፳፭ እናም እነሆ፣ [ሀ]ፀሎታቸውም ደግሞ ጌታ እነዚህን ነገሮች እንዲያመጣ ለፈቀደለት ለእርሱ ጥቅም ነበር።

፳፮ እናም ማንም ሰው እነዚህ ነገሮች አይመጡም በማለት ሊናገር አይገባውም፣ በእርግጥ ይመጣሉና፣ ጌታ ተናግሮታልና፤ በጌታ እጅ ከመሬት ውስጥ [ሀ]ይወጣሉ፣ እናም ማንም ሊገታው አይቻለውም፤ [ለ]ታዕምራቶች ቆመዋል በሚባልበትም በዚያን ቀን ይመጣል፤ እናም ይህም አንድ ሰው [ሐ]ከሞት እንደሚናገር አይነት ሆኖ ይመጣል።

፳፯ እናም [ሀ]በምስጢራዊው ሴራዎች እና በጨለማው ስራዎች የተነሳ የቅዱሳንም [ለ]ደም ወደ ጌታ በሚጮሁበት በዚያን ቀን ይመጣል።

፳፰ አዎን፣ የእግዚአብሔር ኃይል ሲካድና፣ [ሀ]ቤተክርስቲያኖችም ሲረክሱ፣ እናም በልባቸው ኩራት በሚወጠሩበት ቀን ይመጣል፤ አዎን፣ የቤተክርስቲያን መሪዎችና መምህራን በልባቸው ኩራት በሚወጠሩበት፣ የቤተክርስቲያናቸው በሆኑት ሰዎች ላይ በሚመቀኙበትም ቀን ይመጣል።

፳፱ አዎን፣ በዚያን ቀን በባዕድ ምድር ስለ እሳትና፣ ስለኃይለኛ ነፋስ፣ እናም ስለ [ሀ]ጭሱ ጭጋግ [ለ]በሚወራበት ጊዜ ይመጣል።

፴ እናም በተለያዩ ቦታዎችም ደግሞ ስለ [ሀ]ጦርነቶች፣ የጦርነት ወሬዎች እናም የምድር መናወጥ ይሰማሉ።

፴፩ አዎን፣ በምድር ገጽ ላይ ታላቅ መበከል በሚሆንበት ቀን ይመጣል፤ በዚያን ጊዜም ግድያና፣ ዝርፊያና፣ ሀሰት፣ እናም ማጭበርበርና፣ ዝሙት፣ እናም ሁሉም ዓይነት እርኩሰቶች ይኖራሉ፤ በዚያም ጊዜ ብዙዎችም እንዲህ ይላሉ፥ ይህንን አድርጉ ወይም ያንኛውን አድርጉ [ሀ]ምንም አይደለም፣ ምክንያቱም እንደነዚህ ዓይነቶቹን በመጨረሻው ቀን ጌታ [ለ]ይደግፋቸዋልና። ነገር ግን ለእነዚህ አይነቶች ወዮላቸው፣ [ሐ]በመራራ መርዝ እና በዓመፅ እስራት ውስጥ ናቸውና።

፴፪ አዎን፣ በዚያን ቀን፣ ወደ እኔ ኑ፣ እናም በገንዘባችሁም ኃጢአታችሁ ይቅር ይባልላችኋል፣ የሚሉ ቤተክርስቲያናት የሚሰሩበት ቀን ይመጣል።

፴፫ እናንተ ክፉና ጠማሞች እናም አንገተ ደንዳና የሆናችሁ ህዝቦች ሆይ፣ ለራሳችሁ [ሀ]ጥቅም ለማግኘት ስትሉ ቤተክርስቲያንን ለምን ሠራችሁ? በነፍሳችሁ ላይ [ለ]ኩነኔን ያመጣባችሁ ዘንድ ቅዱስ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል ለምን [ሐ]ቀየራችሁት? እነሆ፣ በእግዚአብሔር ራዕይ ላይ ተስፋ አድርጉ፤ እነሆም በዚያን ቀንም እነዚህ ነገሮች ሁሉ የሚፈጸሙበት ጊዜ ይመጣል።

፴፬ እነሆ፣ ጌታ በዚያን ቀን እነዚህ ነገሮች በመካከላችሁ በሚመጡበት ጊዜ በቅርቡ መምጣት ስላለባቸው ታላቅ እና አስገራሚ ነገሮች ለእኔ አሳይቶኛል።

፴፭ እነሆ፣ እናንተ እዚህ እንዳላችሁ አድርጌ እናገራችኋለሁ፣ እናም እናንተ ግን

፳፬ ለ ያዕቆ. ፬፥፮፤
ሔለ. ፲፥፱።
ሐ አልማ ፲፬፥፳፯–፳፱።
፳፭ ሀ ሞር. ፭፥፳፩።
፳፮ ሀ ኢሳ. ፳፱፥፬፤
፪ ኔፊ ፴፫፥፲፫።
ለ ሞር. ፱፥፲፭–፳፮፤
ሞሮኒ ፯፥፳፯–፳፱፤ ፴፫–፴፯።
ሐ ፪ ኔፊ ፳፮፥፲፭–፲፮፤
ሞር. ፱፥፴፤ ሞሮኒ ፲፥፳፯።
፳፯ ሀ ቅ.መ.መ. የሚስጥር ስብሰባ።
ለ ኤተር ፰፥፳፪–፳፬፤
ት. እና ቃ. ፹፯፥፮–፯።
፳፰ ሀ ፪ ጢሞ. ፫፥፩–፯፤
፩ ኔፊ ፲፬፥፱–፲፤
፪ ኔፊ ፳፰፥፫–፴፪፤
ት. እና ቃ. ፴፫፥፬።
፳፱ ሀ ፩ ኔፊ ፲፱፥፲፩፤
ት. እና ቃ. ፵፭፥፴፱–፵፪።
ለ ኢዩ. ፪፥፳፰–፴፪፤
፪ ኔፊ ፳፯፥፪–፫።
፴ ሀ ማቴ. ፳፬፥፮፤
፩ ኔፊ ፲፬፥፲፭–፲፯።
፴፩ ሀ ፪ ኔፊ ፳፰፥፳፩–፳፪።
ለ ፪ ኔፊ ፳፰፥፰።
ሐ አልማ ፵፩፥፲፩።
፴፫ ሀ ቅ.መ.መ. የካህን ተንኮል።
ለ ቅ.መ.መ. ኩነኔ።
ሐ ፩ ኔፊ ፲፫፥፳፮–፳፱።

የላችሁም። ነገር ግን እነሆ፣ ኢየሱስ ክር ስቶስ እናንተን አሳይቶኛል፣ እናም እኔም ስራችሁን አውቃለሁ።

፴፤ እናም በልባችሁ ኩራት ᵐእንደምት ራመዱ አውቃለሁ፤ እናም ከጥቂቶች በስ ተቀር ᵃያማሩ ልብሶችን በመልበስ፣ በመ ቅናትና፣ በፀብ፣ እናም በተንኮልና፣ በስ ቃይ፣ እንዲሁም በሁሉንም ዓይነት ክፋ ቶች በመፈፀም ራሳቸውን በልባቸው ኩራት ᶜከፍ የማያደርጉ የሉም። በልባችሁ ኩራት የተነሳ ቤተክርስቲያኖቻችሁ፣ አዎን፣ እያ ንዳንዱም የተበከለ ሆኗልና።

፴፭ እነሆም፣ እናንተ ᵐገንዘብና፣ ንብረ ቶቻችሁን፣ እናም ያማሩ ልብሶቻችሁንና፣ የቤተክርስቲያኖቻችሁን ማስጌጥ ከድሆች፣ እናም ከተቸገሩት፣ ከታመሙትና ከሚሰ ቃዩት በላይ ትወዳላችሁ።

፴፮ ራሳችሁን ለማይረባ ነገር የሸጣችሁ እናንተ የተበላሻችሁ፣ እናንተ ግብዞች፣ እናንተ መምህራን ሆይ፣ ለምን ቅዱስ የሆ ነውን የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን ትበ ክሉታላችሁ? የክርስቶስን ስም በእራሳቸው ላይ ለመውሰድ ለምን ᵐታፍራላችሁ? በዓ ለም ᵃክብር የተነሳ ከማይጠፋው ᶜስቃይ የበለጠ መጨረሻ የሌለው ደስታ ዋጋው ትልቅ መሆኑን ለምን አታስቡም?

፴፯ እናም የተራቡና፣ የተቸገሩ፣ እናም የታረዙና፣ የታመሙ፣ እንዲሁም ስቃይ ያለባቸው በእናንተ በኩል ሳታስተውሏቸው እንዲያልፉ እየፈቀዳችሁ ህይወት በሌላ ቸው ነገሮች ለምን ራሳችሁን ታስጌጣላ ችሁ?

፴ አዎን፣ ጥቅምን ለማግኘትና ባሏ የሞተ ባት ሴት በጌታ ፊት እንድታዝን፣ እናም ደግሞ አሳዳጊ የሌላቸው በጌታ ፊት እን ዲያዝኑና፣ ደግሞ በእናንተ ላይም ለበቀል ከምድር የአባቶቻቸውና የባሎቻቸው ደም ወደ ጌታ እንዲጮህ ᵐሚስጢራዊውን እር ኩሰት ለምን ትሰራላችሁ?

፴፩ እነሆ፣ የበቀል ጎራዴ በላያችሁ ላይ ያንጥብባል፣ እናም የፃድቃኖችን ደም ᵐበበቀል በእናንተ ላይ የሚመልስበት ጊዜ ወዲያው ይመጣል፣ ከዚህም በኋላ ጩኸ ታቸውን መቋቋም አይችልምና።

ምዕራፍ ፱

ሞሮኒ በክርስቶስ ለማያምኑት ንሰሃ እንዲ ገቡ ጠራቸው—ራዕይ ስለሚሰጠው እናም ለታማኞችም ራዕዮችን እናም ምልክቶ ችን ስለሚሰጠው የተአምራት እግዚአብ ሔር አወጀ—ተአምራቶች የቆሙት እም ነት ባለመኖሩ ነው—ያመኑትን ምልክቶች ይከተሉአቸዋል—ሰዎች ብልህ እንዲሆ ኑና ትዕዛዛቱን እንዲጠብቁ ይመከራሉ። ከ፴፲፭–፴፲፯ ዓ.ም. ገደማ።

፩ እናም አሁን፣ ደግሞ በክርስቶስ ስለማ ያምኑት እናገራለሁ።

፪ እነሆ፣ በመጎብኘታችሁ ቀን ታምናላች ሁን—እነሆ፣ ጌታ ሲመጣ፣ አዎን በዚያ፣ ᵐበታላቁ ቀን ᵃመሬት እንደ ጥቅልል በም ትጠቀለልበት ጊዜ እናም አለቶችም በታ ላቅ ሙቀት ᶜበሚቀልጡበት ጊዜ፣ አዎን፣ በዚያ ታላቅ ቀን በእግዚአብሔር በግ ፊት በምትቆሙ ጊዜ—እግዚአብሔር የለም ትላላችሁን?

፫ ክርስቶስን መካዳችሁን ትቀጥሉበታላ ችሁ፣ ወይንም የእግዚአብሔርን በግ ለማ የት ይቻላችኋል? ጥፋታችሁን እያወቃ ችሁ ከእርሱ ጋር ለመኖር ታስባላችሁን? ህጉን በማንኛውም እንደጣሳችሁ ነፍሳችሁ አውቃ በምትቆስል ጊዜ ከቅዱሱ ጋር በመ

፴፤ *ሀ* ቅ.መ.መ. መራመድ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መራመድ (መሄድ)።
ለ አልማ ፭፡ ፶፫።
ሐ ያዕቆ. ፪፡ ፲፫።
፴፭ *ሀ* ፪ ኔፊ ፳፰፡ ፱–፲፤።
፴፮ *ሀ* ሮሜ ፩፡ ፲፤፣
፪ ጢሞ. ፩፡ ፰፣
፩ ኔፊ ፰፡ ፳፫–፳፰፣
አልማ ፴፤፡ ፳፩።
ለ ፩ ኔፊ ፲፫፡ ፱።
ሐ ሞዛያ ፫፡ ፳፭።
፴ *ሀ* ቅ.መ.መ. የሚስጥር ስብሰባ።
፴፩ *ሀ* ፩ ኔፊ ፳፪፡ ፲፱።
፴፪ ፪ *ሀ* ሚል. ፪፡ ፭፣
፫ ኔፊ ፳፰፡ ፴፩።
ለ ሞር. ፭፡ ፳፫፣
ት.እና ቃ. ፳፫፡ ፳–፳፩።
ቅ.መ.መ. አለም—የአለም መጨረሻ።
ሐ ዓሞ. ፱፡ ፲፫፣ ፫ ኔፊ ፳፤፡ ፫።

ኖር ደስተኛ መሆን እንደምትችሉ ታስባላ ችሁን?

፩ እነሆ፣ የተበከለ ህሊና በፊቱ እያላ ችሁ ከቅዱስ እና ፍትህ እግዚአብሔር ጋር መኖር [ሀ]ከተኮነኑት ነፍሳት ጋር [ለ]በሲዖል ከመኖር በላይ አሰቃቂ ነው እላችኋለሁ።

፪ እነሆም፣ በእግዚአብሔር ፊት [ሀ]ራቁ ታችሁን መሆናችሁን፣ እናም ደግሞ የእ ግዚአብሔር ክብርና፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስነት ለማየት በምትመጡበት ጊዜ፣ በእናንተ ላይ የማይጠፋን እሳት ያቀጣጥ ላል።

፣ እናንተ [ሀ]የማታምኑ ሆይ፣ ወደ ጌታ [ለ]ተመለሱ፤ ምናልባት በመጨረሻውና በዚያ በታላቁ ቀን እንከን የሌላችሁ፣ [ሐ]ንፁህ፣ መልካም፣ እና [መ]በበጉ ደም የፀዳችሁ ሆናችሁ ትገኙ ዘንድ ወደ አብ በኢየሱስ ስም በኃይል ጩሁ።

፤ እናም እናንተ የእግዚአብሔርን ራዕይ [ሀ]ለካዳችሁና፣ እነርሱ ተፈፅመዋል፣ ራዕ ዮች፣ ትንቢቶች፣ ስጦታዎችም ሆነ፣ መፈ ወስ፣ እናም በልሳን መናገርም ሆነ፣ በልሳን የሚናገሩትን [ለ]መተርጎም ቆሟል የምትሉ ትን በድጋሚ እናገራችኋለሁ፤

፭ እነሆ እኔ እንዲህ እላችኋለሁ፣ እነዚህን ነገሮች የሚክድ የክርስቶስን [ሀ]ወንጌል አያ ውቅም፤ አዎን፣ ቅዱሳን መጽሐፍትንም አላነበበም፣ ይህም ቢሆን እንኳን [ለ]አልተ ረዱትም።

፮ እግዚአብሔር [ሀ]ትናንትና፤ ዛሬም እን ዲሁም ለዘለዓለም አንድ እንደሆነ እናም በእርሱም የመቀያየርም ሆነ የመለወጥ ጥላ አለመኖሩን አላነበብንምን?

፯ እናም አሁን፣ ለራሳችሁ የሚለዋወጥና በእርሱም የመለዋወጥ ጥላ ያለበትን አም ላክ የምታስቡ ከሆነ፣ የተአምራት አም ላክ ያልሆነውን አምላክ ለራሳችሁ አስባ ችኋል።

፰ ነገር ግን እነሆ፣ ለእናንተም የተአ ምራት አምላክ፣ እንዲሁም የአብርሃምን አምላክ፣ እናም የይስሃቅን አምላክ፣ እናም የያዕቆብን አምላክን አሳያችኋለሁ፤ እር ሱም ሰማይና ምድርን፣ እናም በውስጡም ያሉትን ነገሮች ሁሉ የፈጠረ [ሀ]አምላክ ነው።

፱ እነሆ፣ እርሱ [ሀ]አዳምን ፈጠረና፣ በአዳም ምክንያት የሰው ልጅ [ለ]ውድቀት መጣ። እናም በሰው ልጅ መውደቅ የተ ነሳ፣ አብና ወልድ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ መጣ፤ እናም በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነ ትም ለሰው ልጅ [ሐ]ቤዛነት መጣ።

፲ እናም በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ለሰዎች ቤዛነት በመምጣቱ፣ ወደ ጌታም ፊት ተመልሰዋል፤ አዎን፣ ሁሉም ሰዎች የዳኑበት በዚህም ነው፥ የክርስቶስ ሞት [ሀ]ትንሣኤን አመጣ፣ ይህም መጨረሻ ከሌ ለው እንቅልፍ ቤዛነት አመጣ፣ መለከቱ ሲነፋ ሰዎች ሁሉ ከዚህ [ለ]እንቅልፍ በእግ ዚአብሔር ኃይል ይነቃሉ፣ እናም ትልል ቆችም ሆኑ ትንንሾች የሆኑት ይመጣሉ፣ እናም ዘላለማዊ ከሆነው የሞት [ሐ]ሰንሰ ለት በመዳንና በመፈታት፣ ይህም ሞት ጊዜአዊው ሞት ነው፣ በፍርዱ ወንበር ፊት ሁሉም ይቆማሉ።

፲፩ እናም የቅዱሱ [ሀ]ፍርድ በእነርሱ ላይ ይመጣል፤ [ለ]ንፁህ ያልሆነውም አሁን ንፁህ ሳይሆን የሚቀርበት ጊዜ ይመጣል፤ እናም

፩ ሀ ቅ.መ.መ. ኩነኔ።
ለ ቅ.መ.መ. ሲ.ዖል።
፪ ሀ ፪ ኔፊ ፱፡፲፡፡
፣ ሀ ቅ.መ.መ. አለማመን።
ለ ሕዝ. ፲፰፡፳፫፣ ፴፪፣ ፡ ት. እና ቃ. ፣፲፡፡ ፡ ሐ ቅ.መ.መ. ንጹህ፣ ንጹህነት።
መ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር በግ።
፤ ሀ ፲ ኔፊ ፳፱፡፲–፣ ለ ፩ ቆሮ. ፲፪፡፣–፲፣ ኢ.አ. ፩፡፣።
፭ ሀ ቅ.መ.መ. ወንጌል።
ለ ማቴ. ፳፪፡፳፱።
፮ ሀ ዕብ. ፲፫፡፡ ፩ ኔፊ ፲፡፲፡–፲፱፣ አልማ ፣፡ ሞሮኒ ፡ ፣ ት. እና ቃ. ፡ ፲፪።
፲፩ ሀ ዘፍጥ. ፩፡፩፣ ሞዛያ ፡ ት. እና ቃ. ፳፣፡ ፡ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ።
፲፪ ሀ ሞዛያ ፲፡ ፡ ሀ ቅ.መ.መ. ፍጥረት፣ የመጨረሻው።
ለ አልማ ፣፡ ፡ ት. እና ቃ. ፡ ፡ ሐ ቅ.መ.መ. ቤዛ፣ ማዳን፣ ቤዛነት።
፲፫ ሀ ሐሌ. ፲፡ ፲–፲፡ ለ ት. እና ቃ. ፡ ሐ ት. እና ቃ. ፣ ፣ ፲፡ ፲፡ ፲፡ ፲ ሀ ቅ.መ.መ. ፍርድ፣ የመጨረሻው።
ለ አልማ ፣፡ ፡ ት. እና ቃ. ፡ ፡ ፡

ፃድቅ የሆነው አሁንም ፃድቅ ይሆናል፤ ደስ
ተኛ የነበረውም አሁን ደስተኛ ይሆናል፤
እንዲሁም ደስተኛ ያልነበረው አሁንም
ደስተኛ አይሆንም።

፲ እናም አሁን፣ እናንተ ለራሳችሁ
ᵇምንም ተአምራትን መስራት የማይችል
አምላክን ያሰባችሁ ሁሉ፣ እንዲህ ስል
እጠይቃችኋለሁ፥ እኔ የተናገርኳቸው እነ
ዚህ ነገሮች ሁሉ አልፈዋልን? መጨረሻው
መጥቷልን? እነሆ አይደለም እላችኋለሁ፤
እናም እግዚአብሔር የተአምራት አምላክ
መሆኑን አላቆመም።

፲፩ እነሆ፣ እግዚአብሔር የሰራቸው በዐ
ይናችን ድንቅ አይደሉምን? አዎን፣ እናም
ድንቅ የሆነውን የእግዚአብሔር ᵇሥራዎች
የሚገባው ማነው?

፲፪ ᵇበቃሉ ሰማይና ምድር ᵃመፈጠሩ፤
እናም ቃሉ ባለው ኃይል የሰው ልጅ ከመ
ሬት ᵃአፈር መፈጠሩ፤ እናም በቃሉ ኃይል
ተአምራት መሠራቱ ተአምር አይደለም
የሚል ማነው?

፲፫ እናም ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ ᵇተአም
ራትን አልሰራም የሚለው ማነው? እናም
በሐዋርያቶቹ እጅ ብዙ ተአምራት ተሰር
ተው ነበር።

፲፬ እናም በዚያ ጊዜ ᵇተአምራቶች ተደ
ርገው ከሆነ፣ እግዚአብሔርስ የተአምራት
አምላክ መሆኑን ለምን ያቆማል እናም ግን
የማይለወጥ አምላክ ሊሆን ይችላል? እን
ዲሁም እነሆ እላችኋለሁ እርሱ አይለወ
ጥም፣ የሚለወጥ ከሆነ አምላክነቱን ያቆ
ማል፣ እናም አምላክነቱን አያቆምም፣ የተ
አምራትም አምላክ ነው።

፲፭ እናም በሰው ልጆች መካከል ᵇተአም
ራት መስራቱን ያቆመበት ምክንያት እነ
ርሱ እምነት አጥተው በመመንመናቸው፣
እናም ከትክክለኛው መንገድ በመራቃቸ
ውና፣ ᵃየሚያምኑበትን አምላክ ባለማወ
ቃቸው ነው።

፲፮ እነሆ፣ እንዲህ እላችኋለሁ ምንም
ባለመጠራጠር በክርስቶስ የሚያምን፣ በክ
ርስቶስ ስም አብን ᵇማንኛውንም ነገር ከጠ
የቀ ለእርሱ ይሰጠዋል፤ እናም ይህ ቃል
ኪዳን ለሁሉም፣ እንዲሁም እስከ አለም
ዳርቻ እንኳን ነው።

፲፯ እነሆም የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ
ክርስቶስ እስከምፅአቱ ለሚቆዩትም ደቀ
መዛሙርቱ፣ አዎን፣ እናም ደግሞ ለሁ
ሉም ደቀመዛሙርት ህዝቡ እየሰሙት እን
ዲህ ሲል ተናገራቸው፥ ወደ ዓለም ሁሉ
ᵇሂዱና፣ ለፍጥረት ሁሉ ወንጌልን ስበኩ።

፲፰ እናም ያመነና የተጠመቀም ይድናል፤
ያላመነ ግን ᵇይኮነናል፤

፲፱ እናም ያመኑትን እነዚህ ᵇምልክቶች
ይከተሏቸዋል—በስሜ ᵃአጋንንትን ያወ
ጣሉ፤ በአዲስ ልሳንም ይናገራሉ፤ መርዛማ
እባቦችንም ያነሳሉ፤ እናም የሚገድልን ነገር
ቢጠጡም አይጎዳቸውም፤ ᵃእጃቸውን በህ
መምተኞች ላይ ይጭናሉና ያድኗቸዋል፤

፲፳ እናም ምንም ሳይጠራጠር በስሜ
የሚያምን ቢኖር፣ ለእርሱ እስከ ዓለም
ዳርቻ ቃሌን ሁሉ ᵇማረጋገጫ አደርግለ
ታለሁ።

፲፳፩ እናም እንግዲህ፣ እነሆ፣ የጌታን ሥራ
የሚቃወም ማን ነው? ንግግሩንስ የሚክድ
ᵇማን ነው? ሁሉን ቻይ በሆነው በጌታ ኃይል
ላይ የሚነሳስ ማን ነው? የጌታን ሥራ የሚ
ንቅ ማን ነው? የክርስቶስን ልጆች የሚንቅስ

፲፭ ᵇ ሞሮኒ ፯፡ ፴፭–፴፯፤
ት. እና ቃ. ፴፭፡ ፰።
ቅ.መ.መ. ተአምራት።
፲፯ ᵇ መዝ. ፴፡ ፭፤
ት. እና ቃ. ፫፯፡ ፻፲፬፤
ሙሴ ፩፡ ፫–፭።
፲፯ ᵇ ያዕቆ. ፬፡ ፱።
ᵃ ቅ.መ.መ. መፍጠር፣
ፍጥረት።
ᵃᵃ ዘፍጥ. ፪፡ ፯፤
ሞዛያ ፪፡ ፳፭።
፲፰ ᵇ ዮሐ. ፮፡ ፲፬።
፲፱ ᵇ ት. እና ቃ. ፳፫፡ ፯–፲።
፳ ᵇ መሳ. ፮፡ ፲፭–፲፫፤
ኤተር ፲፪፡ ፲፪–፲፳፤
ሞሮኒ ፯፡ ፴፭–፴፯።
ᵃ ቅ.መ.መ. መታመን።
፳፩ ᵇ ማቴ. ፳፩፡ ፳፪፤
፫ ኔፊ ፲፳፡ ፳።
፳፪ ᵇ ማር. ፲፮፡ ፲፭–፲፮።
ቅ.መ.መ. የሚስዮን ስራ።
፳፫ ᵇ ቅ.መ.መ. ኩነኔ።
፳፬ ᵇ ማር. ፲፮፡ ፲፯–፲፰።
ቅ.መ.መ. ምልክት።
ᵃ የሐዋ. ፲፮፡ ፲፯–፲፰።
ᵃᵃ ቅ.መ.መ. ለታመሙት
አገልግሎት መስጠት።
፳፭ ᵇ ቅ.መ.መ. ምስክርነት፣
ራዕይ።
፳፮ ᵇ ፫ ኔፊ ፳፱፡ ፱–፲።

ማን ነው? እነሆ፣ የጌታን ሥራ ^የምትንቁ ሁሉ፣ ትገረማላችሁ እናም ትጠፋላችሁ።

፳፯ አቤቱ አትናቁና አትገረሙ፤ ነገር ግን የጌታን ቃላት አድምጡት፣ እናም፣ በስሙም የምትፈልጉትን ነገር አብን በኢ የሱስ ስም ጠይቁት። አትጠራጠሩ፣ ነገር ግን የምታምኑ ሁኑ፣ በጥንት ጊዜ እንደ ነበሩት ሰዎች በእምነት ጀምሩ፤ እናም በሙሉ ^ልባችሁ ሆናችሁ ወደ ጌታ ^ኑ፤ እናም በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ በፊቱ የራ ሳችሁን መዳን ^ፈፅሙ።

፳፰ በሙከራ ጊዜያችሁም ^ብልህ ሁኑ፤ የጎደፉ ነገሮችን በሙሉ ከላያችሁ ላይ አራግፉ፤ ^ለምኞቶቻችሁ ማስፈፀሚያ በክፉ አትጠይቁ፤ ነገር ግን ወደ ፈተና እንዳትገቡ ዘንድ፣ ነገር ግን እናንተ እው ነተኛውን እናም ^ሕያውን እግዚአብሔር ታገለግሉ ዘንድ በማይነቃነቀው ፅናታችሁ ጠይቁ።

፳፱ ^ብቁ ሳትሆኑ እንዳትጠመቁም ተጠ ንቀቁ፤ የክርስቶስንም ቅዱስ ቁርባን ^ብቁ ሳትሆኑ ላለመቁረስ ተጠንቀቁ፤ ነገር ግን ሁሉንም ነገሮች ስታደርጉ ^በብቁነት ማድ ረጋችሁን ተመልከቱ፣ ስታደርጉም በህ ያው እግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስ ቶስ ስም አድርጉት፤ እናም ይህን ካደረጋ ችሁና፣ እስከመጨረሻ ፅኑ ከሆናችሁ በም ንም ዓይነት እናንተ አትጣሉም።

፴ እነሆ፣ ሙታን ሆኜ እንደምናገረው ^እናገራችኋለሁ፤ ምክንያቱም እናንተ የእኔ ቃል እንደሚኖራችሁ አውቃለሁ።

፴፩ ^በጉድለቶቼ ምክንያት አትኮንኑኝ፣ አባቴንም በጉድለቶቼ አትኮንኑት፣ ከእር ሱም በፊት ሲጽፉ የነበሩትንም አትኮንኑ አቸው፤ ነገር ግን እግዚአብሔር እኛ ከነበ ርነው የበለጠ ብልህ ለመሆን ትማሩ ዘንድ ፍፁም አለመሆናችንን ስለገለፀላችሁ ምስ ጋና አቅርቡለት እንጂ።

፴፪ እናም አሁን፣ እነሆ፣ በመካከላችን በንግግራችን ስርዐት መሰረት የተላለፉል ንና የቀየርናቸው ^የተለወጡ ግብፃውያን ተብለው በሚጠሩት ፊደላት እንደችሎታ ችን ይህንን መዝገብ ፅፈናል።

፴፫ እናም ሰሌዳዎቻችን በበቂ ሁኔታ ትልቅ ቢሆኑ ኖሮ በዕብራውያን እንፅፈው ነበር፤ ነገር ግን ዕብራውያንም ደግሞ በእኛ ተለውጧል፤ እናም በዕብራውያን መፃፍ ብንችል ኖሮ፣ እነሆ፣ በመዛግብቶቻችን ውስጥ ስህተት አታገኙም ነበር።

፴፬ ነገር ግን ጌታ የፃፍናቸውን ነገሮች ያውቃል፣ እናም ደግሞ ማንም ሌላ ሰው ቋንቋችንን አያውቅም፤ እናም ምክንያቱም ማንም ሌላ ሰው ቋንቋችንን ባለማወቁ፣ ስለ ዚህ እርሱም የሚተረጉምበትን ^መንገድ አዘጋጅቷል።

፴፭ እናም እነዚህ ነገሮች ^እምነት አጥ ተው የመነመኑትን ወንድሞቻችንን ደም ከልብሶቻችን ላይ እናነፃ ዘንድ የተፃፉ ናቸው።

፴፮ እናም እነሆ፣ ወንድሞቻችንን በተ መለከተ እነዚህን ነገሮች፣ አዎን፣ ክርስ ቶስን ወደማወቅ ይመለሱ ዘንድ፣ ^የፈለ ግናቸው በምድሪቱ ይኖሩ በነበሩት ቅዱ ሳን ሁሉ ፀሎት መሰረት ነው።

፴፯ እናም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም ፀሎ ታቸው እንደ እምነታቸው እንዲመለስላ ቸው ያድርግ፤ እግዚአብሔር አብም ከእስ ራኤል ቤት ጋር የገባውን ቃል ኪዳን ያስታ ውስ፤ እናም በክርስቶስ ስም ባላቸው እም ነት በኩል ለዘለዓለም ይባርካቸው። አሜን።

፳፤ ^ለ ምሳ. ፲፫፡፲፫።
፳፯ ^ሀ ኢ.ያ. ፳፪፡፭፣
ት. እና ቃ. ፳፬፡፳፪፣ ፴፩።
ቅ.መ.መ. ልብ።
^ለ ሞሮኒ ፲፡፴–፴፪።
^ሐ ፊልጵ. ፪፡፲፪።
፳፰ ^ሀ ያዕቆ. ፤፡፲፪።
^ለ ቅ.መ.መ. ምኞት።
^ሐ አልማ ፭፡፲፫።
፳፱ ^ሀ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣
መጥመቅ—ለመጠመቅ
ብቁነት።
^ለ ፩ ቆሮ. ፲፩፡፳፯–፴፣
፣ ኔፊ ፲፡፳፡፳፰–፴፪።
^ሐ ቅ.መ.መ. ብቁ፣ ብቁነት።
፴ ^ሀ ሞር. ፡፡፳፤፣
ሞሮኒ ፲፡፳፤።
፴፩ ^ሀ ሞር. ፡፡፲፣፣
ኤተር ፲፪፡፳፪–፳፰፣ ፴፭።
፴፪ ^ሀ ፩ ኔፊ ፩፡፪፣
ሞዛያ ፩፡፬።
፴፫ ^ሀ ሞዛያ ፡፡፣ ፲፫–፲፡፣
ኤተር ፫፡፳፫፣ ፳፡፣
ት. እና ቃ. ፲፯፡፩።
፴፭ ^ሀ ፪ ኔፊ ፳፤፡፲፭።
፴፮ ^ሀ ሞር. ፡፡፡፬–፳፤፣
ት. እና ቃ. ፲፡፴፤–፴፪።

መፅሐፈ ኤተር

በንጉስ ሞዛያ ዘመን በሊምሂ ሰዎች ከተገኙት ከሃያ አራቱ ሠሌዳዎች ላይ የተወሰደ የያሬዳውያን ታሪክ።

ምዕራፍ ፩

ሞሮኒ የኤተርን ፅሁፍ አሳጠረ—የኤተር የትውልድ ሐረግ ተዘርዝሯል—በባቢሎ ናውያን ግንብ ወቅት የያሬዳውያን ቋንቋ አልተቀላቀለም—ጌታ ወደ ተመረጠች ምድር እንደሚመራቸው እናም ታላቅ ሀገር እንደሚያደርጋቸው ቃል ገብቷል።

፩ እናም እንግዲህ፣ እኔ [a]ሞሮኒ፣ ከዚህች ሃገር ከሰሜን በኩል በጌታ [b]እጅ ጠፍ ተው የነበሩትን የጥንት ሰዎች ታሪክ መስ ጠቴን እቀጥላለሁ።

፪ እናም መፅሐፈ ኤተር ከተባለው በሌምሂ ሰዎች ከተገኘው [c]ከሃያ አራተ ኛው ሠሌዳ ላይ የራሴን ዘገባ እወስዳለሁ።

፫ እናም ስለዓለም መፈጠር የሚያወ ራው፣ እናም ደግሞ ስለአዳም፣ እናም ከዚ ያን ጊዜ ጀምሮ እስከ ታላቁ [d]ግንብ ድረስ ያለው ታሪክ፣ እናም እስከዚያም ጊዜ ድረስ በሰው ልጆች መካከል የሆኑት ማናቸው ንም ነገሮች የያዘው የዚህ መዝገብ የመጀ መሪያ ክፍል እኔ እንደምገምተው በአይሁ ዶች መካከል ይገኛል—

፬ ስለዚህ [e]ከአዳም ዘመን ጀምሮ እስከዚ ያን ጊዜ የተከናወኑትን ነገሮች አልፅፍም፤ ነገር ግን በሰሌዳዎቹ ላይ አሉ፤ እናም እነ ርሱን ያገኘ ታሪኩን በሙሉ ያውቅ ዘንድ ኃይል ይኖረዋል።

፭ ነገር ግን እነሆ፣ እኔ ታሪኩን በሙሉ አልናገርም፣ ነገር ግን ከግንብ ጀምሮ እስ ከጠፉበት ጊዜ ድረስ ያለውን የታሪክ ክፍል ብቻ እሰጣለሁ።

፮ እናም በዚህ መንገድ ዘገባውን እሰጣ ለሁ። ይህንን ታሪክ የፃፈው [f]ኤተር ነበር፣ እናም እርሱም የቆሪያንቶር ወገን ነበር።

፯ ቆሪያንቶር የሞሮን ልጅ ነበር።

፰ እና ሞሮንም የኤተም ልጅ ነበር።

፱ እናም ኤተም የአሃህ ልጅ ነበር።

፲ አሃህ የሴት ልጅ ነበር።

፲፩ እና ሴት የሺብሎን ልጅ ነበር።

፲፪ እና ሺብሎን የቆም ልጅ ነበር።

፲፫ እና ቆም የቆሪያንቱም ልጅ ነበር።

፲፬ እና ቆሪያንቱምም የአምኒጋዳ ልጅ ነበር።

፲፭ እና አምኒጋዳ የአሮን ልጅ ነበር።

፲፮ እና አሮን የሔርቶም ልጅ የነበረው የሔት ወገን ነበር።

፲፯ እና ሔርቶም የሊብ ልጅ ነበር።

፲፰ እና ሊብ የኪሽ ልጅ ነበር።

፲፱ እና ኪሽም የቆሮም ልጅ ነበር።

፳ ቆሮም የሌዊ ልጅ ነበር።

፳፩ እና ሌዊ የቂም ልጅ ነበር።

፳፪ እና ቂም የሞሪያንተን ልጅ ነበር።

፳፫ እና ሞሪያንተን የሪፕላኪሽ ወገን ነበር።

፳፬ እና ሪፕላኪሽ የሼዝ ልጅ ነበር።

፳፭ እና ሼዝ የሔት ልጅ ነበር።

፳፮ እና ሔት የቆም ልጅ ነበር።

፳፯ እና ቆም የቆሪያንቱም ልጅ ነበር።

፳፰ እና ቆሪያንቱም የኤመር ልጅ ነበር።

፳፱ እና ኤመር የኦመር ልጅ ነበር።

፴ እና ኦመር የሹል ልጅ ነበር።

፴፩ እና ሹል የቂብ ልጅ ነበር።

፴፪ እናም ቂብም የያሬድ ልጅ የነበረው የኦሪያ ልጅ ነበር።

፩ ፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. ሞሮኒ፣ የሞርሞን ልጅ።
ለ ሞር. ፭፡፳፫፣ ት.እና ቃ. ፲፯፡፲–፲፡።
፪ *ሀ* አልማ ፴፯፡፳፩፣ ፳፩፣ ኤተር ፲፫፡፲፩፡ ፲፭፡ ፴፡።
፫ *ሀ* ኦምኒ ፩፡፳፪፣ ሞዛያ ፳፰፡፲፯፣ ሔለ. ፣፡፳፰፡።
፬ *ሀ* ይህም በኦሪት ዘፍጥረት ፩–፲ አንድ አይነት ጊዜዎችን የሚሸፍን ማለት ነው።
፯ *ሀ* ኤተር ፲፪፡፪፣ ፣ ፲፭፡ ፴፡።

፴፫ ጌታ የህዝቡን ቋንቋ ᵐበቀላቀለበት
እናም በምድሪቱ ᵃገፅ ሁሉ ላይም እንዲ
ሠራጨ በቁጣው በማለ ጊዜ ከታላቁ ግንብ
ᵃያሬድ ከወንድሞቹ፣ እናም ከቤተሰቦቹ
ጋር በመሆን ከሌሎች እና ከቤታሰቦቻቸው
ጋር መጣ፣ እናም እንደጌታ ቃልም ህዝቡ
ተበትኖ ነበር።

፴፬ እናም ᵐየያሬድ ወንድም ትልቅ እናም
ኃያል ሰው በመሆኑ፣ እናም በጌታም በይ
በልጥ የሚወደድ በመሆኑ፣ ያሬድ ወንድ
ሙም እንዲህ ሲል ተናገረው፡ የተናገር
ነውንም እንዳንረዳ እርሱ የምንናገረውን
እንዳይቀላቅልብን ወደ ጌታ ጩህ።

፴፭ እናም እንዲህ ሆነ የያሬድ ወንድም
ወደ ጌታ ጮኸ፣ እናም ጌታም ለያሬድ
አዘነለት፤ ስለዚህ የያሬድን ቋንቋ አልቀ
ላቀለበትም፤ እናም የያሬድና የወንድሙ
ቋንቋ አልተቀላቀለባቸውም።

፴፮ ከዚያም ያሬድ ለወንድሙ እንዲህ
አለ፡ እናም ከወዳጆቻችንም ላይ ቁጣውን
ይመልስ ዘንድ ቋንቋቸውን እንዳይቀላቅል
ባቸው በድጋሚ ወደ ጌታ ጩህ።

፴፯ እናም እንዲህ ሆነ የያሬድ ወን
ድም ወደ ጌታ ጮኸ፣ እናም ጌታ ለወዳ
ጆቹ እናም ደግሞ ለቤተሰቦቹ ራራላቸው፣
ስለዚህ ቋንቋቸውን አልቀላቀለባቸውም።

፴፰ እናም እንዲህ ሆነ ያሬድ ለወንድሙ
በድጋሚ እንዲህ ሲል ተናገረ፡ ሂድ እናም
ጌታ ከምድሪቱ ወዴት እንደሚያስወጣን
ጠይቀው፤ እናም ከምድሪቱ የሚያስወጣን
ከሆነ ወዴት መሄድ እንዳለብን ወደ እርሱ
ጩህ። እናም ምናልባት ከምድር ሁሉ ወደ
ᵐተመረጠችው ስፍራ ጌታ እንደሚወስደን
ማን ያውቃል? እናም እንደዚያ የሚሆን
ቢሆን ለውርሳችን እንቀበለው ዘንድ ለጌታ
ታማኞች እንሁን።

፴፱ እናም እንዲህ ሆነ በያሬድ አንደበት
በተነገረው መሰረት የያሬድ ወንድም ወደ
ጌታ ጮኸ።

፴ እናም እንዲህ ሆነ ጌታ የያሬድን ወን
ድም ሰማው፣ እናም ለእርሱም አዘነለት፣
እናም እንዲህ ሲል ተናገረው፡

፴፩ ሂድ እናም መንጋዎቻችሁን ሴት
እናም ወንድ የሆኑትን ከሁሉም ዓይነት
በአንድ ላይ ሰብስብ፤ እናም ደግሞ በም
ድር ላይ ካሉት ዘር ፍሬዎች ከሁሉም ዓይ
ነት ያሉትን፤ እናም ᵐቤታሰቦችህን፤ እናም
ደግሞ ወንድምህን ያሬድ እና ቤተሰቡን፤
እናም ደግሞ ᵃወዳጆችህን እና ቤተሰቦቻች
ውን፣ እናም የያሬድን ወዳጆች እናም ቤተ
ሰቦች በሙሉ በአንድነት ሰብስብ።

፴፪ እናም ይህንን በምታደርግበት ጊዜ
ከፊታቸው በመሆን በስተሰሜን ወዳለው
ሸለቆ አብረሃቸው ᵐትጓዛለህ። እናም እዚያ
ቦታም አገኝህለሁ፣ እናም ከምድሪቱ ሁሉ
በላይ ወደ ᵃተመረጠችው ስፍራም በምት
ሄድበትም ጊዜ ᵐከፊትህ እሄዳለሁ።

፴፫ እናም እዚያ አንተንና ዘሮችህን እባ
ርካለሁ፣ እናም ከዘሮችህም፣ እናም ከወ
ንድምህ ዘር፣ እናም ከአንተ ጋር ከሚሄዱ
ትም፣ ለራሴ ታላቅ ሀገር አስነሳለሁ። እናም
ከምድር ገፅ ላይ ሁሉ ከአንተ ዘር ለራሴ
ካበዛኋቸው የበለጠ ታላቅ ሀገር አይኖርም።
እናም ይህንንም አደርግልሃለሁ ምክንያ
ቱም ለነዚህ ለረጅም ጊዜያት ወደ እኔ ስለ
ጮህክ ነው።

ምዕራፍ ፪

*ያሬዳውያን ወደ ቃል ኪዳን ምድር ለመ
ጓዝ ተዘጋጁ—ይህችም ሰዎች ክርስቶስን
ማገልገል ያለባቸው የተመረጠች ምድር
ናት አለበለዚያም ይወገዳሉ—ጌታም
ለያሬድ ወንድም ለሦስት ሰዓታት ያህል
ተናገረው—ያሬዳውያን ጀልባዎችን
ሰሩ—ጌታም የያሬድ ወንድም እንዴት
ጀልባዎቹ ብርሃን ማግኘት እንደሚችሉ
ሃሳቡን እንዲያቀርብ ጠየቀው።*

፴፫ ሀ ዘፍጥ. ፲፩፡፮–፱።
ለ ሞዛያ ፳፰፡፲፯።
ሐ ቅ.መ.መ. ያሬድ።
፴፬ ሀ ቅ.መ.መ. የያሬድ ወንድም።

፴፭ ሀ ቅ.መ.መ. የቃል ኪዳን
ምድር።
፴፩ ሀ ኤተር ፮፡፳።
ለ ኤተር ፮፡፲፯።

፴፪ ሀ ፩ ኔፊ ፪፡፩–፪፤
አብር. ፪፡፲።
ለ ፩ ኔፊ ፲፫፡፴።
ሐ ት. እና ቃ. ፹፬፡፹፭።

፩ እናም እንዲህ ሆነ ሴት እናም ወንድ ከሆኑት ከሁሉም ዓይነት በአንድ ላይ ከሰ በሰቧቸው ከመንጋዎቻቸው ጋር ያሬድ እና ወንድሙ፣ እናም ቤተሰቦቻቸው፣ እናም ደግሞ የያሬድ ወዳጆች፣ እናም ወንድሞቹ እና የእርሱ ቤተሰቦች፣ በሸለቆው በስተሰ ሜን በኩል ሄዱ፤ (እና ሸለቆውም በኃያሉ አዳኝ ስም "ናምሩድ ተብሎ ይጠራ ነበር)።

፪ እናም ደግሞ ወጥመድ ዘረጉ እናም የሰ ማይ አዕዋፋትን ያዙ፤ እናም መንጠቆአቸ ውን ደግሞ አዘጋጁ፣ በእነዚህም የውሀዎ ችን ዓሣ ተሸከሙ።

፫ እናም እነርሱ ደግሞ በትርጉም የንብ ቀፎ የሚባለውን ደዘረት ተሸክመው ነበር፤ እናም የንብ መንጋዎችን እናም በምድር ላይ ያሉትን ነገሮች ሁሉ፣ የሁሉም አይነት ዘሮ ችን እንደዚህ ተሸክመው ነበር።

፬ እናም እንዲህ ሆነ ወደ ናምሩድ ሸለቆ በወረዱ ጊዜ ጌታ መጣ እናም ከያሬድ ወን ድም ጋር ተነጋገረ፤ እናም እርሱ "በደመና ውስጥ ነበር፣ እናም የያሬድ ወንድምም አላየውም።

፭ እናም እንዲህ ሆነ ጌታም ከዚህ በፊት ማንም ሰው ሰፍሮበት ወዳልነበረበት ሥፍራ ወደ ምድረበዳው እንዲሄዱ አዘዛቸው፤ እናም እንዲህ ሆነ ጌታም መራቸው፤ እናም "በደመና ውስጥ ቆሞ አነጋገራቸው፣ እናም ወዴት መሔድ እንዳለባቸውም አቅጣጫ ውን አሳያቸው።

፮ እናም እንዲህ ሆነ በምድረበዳው ውስጥ ተጓዙ፣ እናም ያለማቋረጥም በጌታ እጅ በመመራት፣ ብዙ ውሀዎችን ያቋረጡበ ትን ጀልባ ሰሩ።

፯ እናም ጌታ ከባህሩ ባሻገር ወዳለው ምድረበዳ እንዲቆሙ አልፈቀደላቸውም፣ ነገር ግን ወደ "ቃል ኪዳን ምድር እንዲ መጡ ይፈልግ ነበር፤ ምድሪቷም ከሌሎች ቦታዎች በላይ የተመረጠች ነበረች፤ ጌታ አምላክም ፃድቅ ለሆኑ ሰዎች ያስቀመጣት ነበረች።

፰ እናም ይህችን የቃል ኪዳን ምድር የራሱ ያደረገ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ ዘለዓለም እውነተኛ እናም አንድ የሆነ ውን አምላክ "ማገልገል እንዳለበት ለያ ሬድ ወንድም በቁጣው ማለለት፤ አለበለ ዚያ የቁጣው ሙላት በደረሰ ጊዜ እነርሱ "ይወገዳሉ።

፱ እናም እንግዲህ፣ ይህችን ምድር በተ መለከተ የቃል ኪዳን ምድር ስለመሆንዋ የእግዚአብሔርን ድንጋጌ ለመመልከት ይቻለናል፤ እናም ማንም ይህችን ምድር የራሱ ያደረገ ሀገር እግዚአብሔርን ያገለ ግላል፣ አለበለዚያ የቁጣው ሙላት በእነ ርሱ ላይ በሆነ ጊዜ ይወገዳሉ። እናም በክ ፋት በተሞሉ ጊዜም የቁጣው መዓት በእነ ርሱ ላይ ይሆናል።

፲ እነሆም፣ ይህች ምድር ከሌሎች ምድ ሮች ሁሉ በላይ የተመረጠች ናት፤ ስለዚህ የያዛት ሁሉ እግዚአብሔርን ያገለግላል አለ በለዚያ ይወገዳል፤ ምክንያቱም ይህ ዘለዓ ለማዊ የሆነ የእግዚአብሔር ድንጋጌ ነውና። እናም ምድሪቱ በሰው ልጆች መካከል "በክ ፋት በተሞላች ጊዜ ነው "የሚወገዱት።

፲፩ እናም "አህዛብ ሆይ ፍፃሜው እስከ ሚደርስ ንሰሃ እንድትገቡ እናም ክፋታች ሁን ታቆሙ ዘንድ፤ ስለዚህ የምድሪቱ ነዋ ሪዎች ከዚህ ቀደም እንዳደረጉት የእግዚአ ብሔር ቁጣ ሙሉንት በራሳችሁ ላይ እን ዳይመጣ የእግዚአብሔርን ድንጋጌ ታውቁ ዘንድ ይህ ለእናንተ ይመጣል—

፲፪ እነሆ፣ ይህች የተመረጠች ምድር ናት፣ እናም በጻፍናቸው ነገሮች የተገለ ፀውን የምድሪቷን አምላክ ኢየሱስ ክርስ ቶስን "ካገለገሉ፣ ምድሪቷን የያዘ ማንኛ

፪ ፩ ሀ ዘፍጥ. ፲፡፳።
፬ ፩ ሀ ዘኁል. ፲፩፡፳፭፤ ት. እና ታ. ፴፬፡፯–፱፤ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፳፰።
፭ ፩ ሀ ዘፀአ. ፲፫፡፳፭–፳፪።
፯ ፩ ፩ ኔፊ ፱፡፲፬።
ቅ.መ.መ. የቃል ኪዳን ምድር።
፰ ፩ ሀ ኤተር ፲፫፡፪።
ለ ፲ረም ፩፡፫፣ ፲፤ አልማ ፴፯፡፳፰፣ ኤተር ፱፡፳።
፲ ሀ ፪ ኔፊ ፳፰፡፲፯።
ለ ፩ ኔፊ ፲፯፡፴፯–፴፰።
፲፩ ሀ ፪ ኔፊ ፳፰፡፴፪።
፲፪ ሀ ኢሳ. ፳፡፲፪።

ውም ሀገር ከባርነት እናም ከምርኮ፣ እናም ከሰማይ በታች ካሉት ሌሎች ሀገሮች ^ነፃ ይሆናል።

፲፫ እናም እንግዲህ ታሪኬን እቀጥላለሁ፤ እነሆም፣ እንዲህ ሆነ ጌታም ያሬድን፣ እና ወንድሙን ምድሪቷን ወደ ከፈለው ወደ ታላቁ ባሕር አመጣቸው። እናም ወደ ባሕሩም በመጡ ጊዜ ድንኳናቸውን ተከሉ፤ እናም የቦታውን ሥም ሞሪያንኩመር ብለው ጠሩት፤ እናም በድንኳኑ ኖሩ፣ እናም ለአራት ዓመታት ያህልም በባህሩ ዳርቻ በድንኳን ኖሩ።

፲፬ እናም እንዲህ ሆነ በአራተኛው ዓመት መጨረሻ ጌታ በድጋሚ ወደ ያሬድ ወንድም መጣ፣ እናም በዳመናው ውስጥ ቆሞ ከእርሱ ጋር ተነጋገረ። እናም ጌታም ለሦስት ሰዓታት ያህል ከያሬድ ወንድም ጋር ተነጋገረ፣ እናም የጌታን ሥም ^ለመጥራት ባለማስታወሱ ^ገሰፀው።

፲፭ እናም የያሬድ ወንድም ለሰራው ክፋት ንሰሃ ገባ፤ እናም ከእርሱ ጋር ለነበሩት ወንድሞቹ ሲል የጌታን ሥም ጠራ። እናም ጌታ እንዲህ አለው፥ አንተን እናም ወንድሞችህን ስለኃጢአታቸው ይቅር እላቸዋለሁ፤ ነገር ግን ከእንግዲህ ኃጢያት አትስራ፤ ^መንፈሴ ሁል ጊዜ ከሰዎች ጋር ^እንደማ ይሆንም አስታውስ፤ ስለዚህ እስከምትበ ስል ኃጢያት ከሰራህ ከጌታ ፊት ተለይተህ ትጠፋለህ። እናም ውርስ በምሰጥህ ምድር ላይ ያሉኝ ሀሳቦች እነዚህ ናቸው፤ ምክን ያቱም ይህች ከሌሎች ምድሮች ሁሉ በላይ ^የተመረጠች ምድር ናትና።

፲፮ እናም ጌታ እንዲህ አለ፥ ሂድ እናም ከዚህ በፊት እንደሰራኸው አይነት ጀል ባን ሥራ። እናም እንዲህ ሆነ የያሬድ ወንድም እናም ደግሞ ወንድሞቹ ወደሥራ ቸው ሔዱ፣ እናም ጌታ ^እንዳዘዛቸው ቀደም ሲል እንደሰሩት አድርገው ጀልባ ዎችን ሰሩ። እናም ትንንሽ ነበሩ፣ እናም ወፍ በውሃ ላይ እንደሚቀለው ያህል እነር ሱም በውሃ ላይ ቀላል ነበሩ።

፲፯ እናም እነዚህም በጣም ^ጥብቅ ሆነው ተሰርተዋል፣ እንዲሁም ልክ እንደ ማህን ውሃ ለመያዝ ይችሉ ነበር፤ እናም ሥራቸ ውም ልክ እንደሳህን የጠበቀ ነበር፤ እናም ጎኖቹም እንደሳህን የጠበቁ ነበሩ፤ እናም ጫፎቹም የሾሉ ነበሩ፤ እናም ላዩ እንደሳ ህን የጠበቀ ነበር፤ እናም እርዝመቱም የዛፍ እርዝማኔን ያክል ነበር፤ እናም መዝጊያው በሚዘጋበት ጊዜም እንደሳህን የጠበቀ ነበር።

፲፰ እናም እንዲህ ሆነ የያሬድ ወን ድም ወደ ጌታ እንዲህ ሲል ጮኸ፥ ጌታ ሆይ ያዘዝከኝን ሥራዎች አከናውኛለሁ፤ እናም እንደመራኸኝም አድርጌ ጀልባዎ ችን ሠርቻለሁ።

፲፱ እናም እነሆ፣ አቤቱ ጌታ፣ በውስ ጣቸው ብርሃን የለም፤ ወዴት እንቅዘፍ? እናም ደግሞ በውስጣቸው ካለው አየር በስ ተቀር ለመተንፈስ ስለማንችል ልንሞት እንችላለን፤ ስለዚህ እንሞታለን።

፳ እናም ጌታ ለያሬድ ወንድም እንዲህ ሲል ተናገረው፥ እነሆ፣ ከላይና ከታች ቀዳዳ ታበጃለህ፤ እናም አየር በምታጣ ጊዜም ቀዳዳውን ከፍተህ አየር ታገኛለህ። እናም ውሃው ወደ አንተ ከመጣብህ፣ እነሆ፣ በጥፋት ውሀ እንዳትጠፋ ቀዳዳ ውን ትደፍነዋለህ።

፳፩ እናም እንዲህ ሆነ የያሬድ ወንድም ጌታ ባዘዘው መሰረት አደረገ።

፳፪ እናም በድጋሚ ወደ ጌታ እንዲህ በማ ለት ጮኸ፥ አቤቱ ጌታዬ እነሆ ያዘዝከኝን አድርጌአለሁ፤ ለህዝቤም ጀልባዎችን አዘ ጋጅቻለሁ፣ እናም እነሆ በውስጣቸውም ብርሃን የለም። እነሆ አቤቱ ጌታዬ ይህንን ታላቅ ውሃ በጨለማው እንድናቋርጥ ትፈ ቅዳለህን?

፲፪ *ለ* ቅ.መ.መ. መብት።
፲፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. ጸሎት።
ለ ቅ.መ.መ. መገሰጽ፣ ተግሳጽ።
፲፭ *ሀ* ኤተር ፲፭፡፲፱።

ለ ዘፍጥ. ፮፡፲፣
፪ ኔፊ ፳፯፡፲፭፤
ሞር. ፭፡፲፮።
ሐ ኤተር ፱፡፳።

፲፯ *ሀ* ፩ ኔፊ ፲፯፡፱–፳፩።
፲፯ *ሀ* ኤተር ፮፡፯።

፳፫ እናም ጌታ ለያሬድ ወንድም እንዲህ ሲል ተናገረው፥ በጀልባው ውስጥ ብርሃን እንዲኖር ምን እንዳደርግልህ ትፈልጋለህ? እነሆም፣ መስኮት ሊኖረው አይችልም፣ ምክንያቱም ትሰባበራላችሁና፤ በእሳት ብርሃን መሄድ ስለሌለባችሁ እሳትም ለመያዝ አትችሉም።

፳፬ እነሆ፣ በባሕሩ መሃል እንደአሳ ነባሪ ትሆናላችሁ፤ እንደተራራ ከፍ የሚለውም ማዕበል ያጋጫችኋል። ይሁን እንጂ በድጋሚ ከባህሩ ውስጥ አወጣችኋለሁ፤ ምክንያቱም [ሀ]ነፋሱ ከአፌ የሚመጣ ነውና፣ እናም ደግሞ [ለ]ዝናቡንና ጎርፉን እኔ ልኬዋለሁና።

፳፭ እናም እነሆ፣ ከእነዚህ ነገሮች እንድትጠበቁ አዘጋጃችኋለሁ፤ ለባህሩ ማዕበል፣ እናም የሚመጣውን ነፋስ፣ እናም የሚመጣባችሁን የጥፋት ውሀ እኔ ካላዘጋጀኋችሁ በቀር ይህንን ጥልቅ ባህር ልታቋርጡት አትችሉም። ስለዚህ በባህሩ ጥልቅ ስትሰጥሙ ብርሃን ታገኙ ዘንድ ምን እንዳደርግልህ ትፈልጋለህ?

ምዕራፍ ፫

የያሬድ ወንድም የጌታን ጣት አስራ ስድስቱን ድንጋዮች ሲነካ ተመለከተ—ክርስቶስ የመንፈስ አካሉን ለያሬድ ወንድም አሳየው—ፍፁም እውቀት ያላቸው በመጋረጃው ሊታገዱ አይችሉም—ተርጓሚዎች የያሬዳውያንን መዝገብ ወደ ብርሃኑ ለማምጣት ተዘጋጅተዋል።

፩ እናም እንዲህ ሆነ የያሬድ ወንድም ተራራውም እጅግ ከፍ ያለ በመሆኑ ሼለም ተብሎ ወደሚጠራው ተራራ ሔደ (እንግዲህ የተዘጋጀው ጀልባ ብዛት ስምንት ነበር) እናም ከአለት አስራ ስድስት ትናንሽ ድንጋዮች አቅልጦ አወጣ፤ እናም እነርሱም የነጡ፣ እናም እንደመስታወት ብሩህ ነበሩ፤ እናም እርሱም ተሸክሞ ወደ ተራራው ጫፍ ወሰዳቸው፣ እናም ወደ ጌታ በድጋሚ እንዲህ ሲል ጮኸ፥

፪ አቤቱ ጌታዬ በጥፋት ውሀ መከበብ አለባችሁ ብለሃል። እንግዲህ እነሆ ጌታ ሆይ፣ አገልጋይህ በፊትህ ደካማ በመሆኑ አትቆጣው፤ ምክንያቱም አንተ ቅዱስ እንደሆንክ እናም በሰማይ እንደምትኖር፤ እናም እኛ ባንተ ፊት ከንቱዎች እንደሆንን እናውቃለን፤ [ሀ]በውድቀትም የተነሳ [ለ]ተፈጥሮአችን ያለማቋረጥ ክፉ ሆኗል፤ ይሁን እንጂ፣ ጌታ ሆይ፣ እንደፈለግነውም ከአንተ እንቀበል ዘንድ አንተን እንድንጠራ ትዕዛዝ ሰጥተኸናል።

፫ እነሆ፣ ጌታ ሆይ፣ በክፉታችን ቀጥተኸናል፣ እናም አባረኸናል፣ እናም ለእነዚህ ብዙ ዓመታትም በምድረበዳው ነበርን፤ ይሁን እንጂ፣ አንተ ለእኛ [ሀ]መሃሪ ነህ። አቤቱ ጌታ፣ በአዘኔታም ተመልከተኝ፣ እናም ከህዝብህም ቁጣህን መልስ፣ እናም በዚህ ማዕበላዊ ባህር በጨለማ እንዲጓዙ አትፍቀድ፤ ነገር ግን ከድንጋይ ያቀለጥኳቸው እነዚህ ነገሮች ተመልከት።

፬ እናም ጌታ ሆይ፣ [ሀ]ስልጣን ሁሉ እንዳለህ፣ እናም ለሰዎች ጥቅምም ማንኛውንም ማድረግ እንደምትችል አውቃለሁ፤ ስለዚህ አቤቱ ጌታ፣ እነዚህን ድንጋዮች በጣትህ ንካቸው፣ እናም በጨለማም እንዲያበሩ አዘጋጃቸው፤ እናም ባዘጋጀነው ጀልባ ላይም ባህሩን በምናቋርጥበት ጊዜ ብርሃን ይሰጡን ዘንድ ያበሩልናል።

፭ እነሆ፣ ጌታ ሆይ፣ ይህንን ማድረግ ትችላለህ። ሰዎች በአስተሳሰባቸው አነስተኛ አድርገው የሚያዩትን ታላቅ ኃይል [ሀ]ለማሳየት እንደምትችል እናውቃለን።

፮ እናም እንዲህ ሆነ የያሬድ ወንድም እነዚህን ቃላት በተናገረ ጊዜ፣ እነሆ፣ [ሀ]ጌታ እጁን ዘርግቶ ድንጋዮቹን አንድ በአንድ

፳፬ ሀ ኤተር ፮፥፭።
ለ መዝ. ፻፵፰፥፰።
፫ ፪ ሀ ቅ.መ.መ. የአዳም እና የሔዋን ውድቀት።
ለ ሞዛያ ፫፥፲፱።
፫ ሀ ኤተር ፩፥፴፬–፵፫።
፬ ሀ ቅ.መ.መ. ሀይል።
፭ ሀ ኢሳ. ፶፭፥፰–፱፤
፩ ኔፊ ፲፮፥፳፱።
፮ ሀ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ።

በጣቱ ነካቸው። እናም ᵃመጋረጃው ከያሬድ ወንድም ዐይን ላይ ተወገደ፣ እናም የጌታን ጣት ተመለከተ፤ እናም ይህ ሥጋና ደም እንደለበሰ እንደ ሰው ጣት ነበር፤ እናም የያሬድ ወንድም በፍርሃት በመዋጡ በጌታ ፊት ወደቀ።

፯ እናም ጌታ የያሬድ ወንድም በመሬት ላይ መውደቁን ተመለከተ፤ እናም ጌታ እን ዲህ ሲል ተናገረ፡ ተነሳ ለምን ትወድቃለህ?

፰ እናም ለጌታ እንዲህ አለው፡ የጌታን ጣት ተመለከትኩ፣ እናም ይመታኛል ብዬ ፈራሁኝ፤ ምክንያቱም ጌታ ሥጋና ደም እንዳለውም አላውቅም ነበርና።

፱ እናም ጌታ እንዲህ አለው፡ በእምነትህ የተነሳ ᵇሥጋና ደም እንደምለብስ ተመለ ከትህ፤ እናም ከዚህ በፊት ማንም ሰው እን ደአንተ ያለ ታላቅ እምነት ያለው በጭራሽ በፊቴ አልመጣም፤ ይህ ባይሆን ኖሮ ጣቴን ለማየት አትችልም ነበር። ከዚህ የበለጠን ነገር አይተሃልን?

፲ እርሱም እንዲህ ብሎ መለሰለት፣ አላየ ሁም፤ ጌታ ሆይ፣ ራስህን አሳየኝ።

፲፩ እናም ጌታ እንዲህ አለው፡ የምናገር ህን ቃላት ታምናለህን?

፲፪ እናም እርሱ እንዲህ ሲል መለሰለት፡ አዎን፣ ጌታ ሆይ፣ አንተ እውነት እንደም ትናገር አውቃለሁ፤ አንተ የእውነት አም ላክ ነህና፣ ᵇለመዋሸት አትችልም።

፲፫ እናም እርሱም እነዚህን ቃላት በተ ናገረ ጊዜ፣ እነሆ፣ ጌታ ራሱን ᵇአሳየው፣ እናም እንዲህ አለው፡ እነዚህን ነገሮች ᵃበማወቅህ አንተ ከመውደቅ ድነሃል፤ ስለ ዚህ እኔ ባለሁበት ተመልሰሀል፣ ስለዚህም ራሴን ᶜአሳይቼሀለሁ።

፲፬ እነሆ፣ ከዓለም መፈጠር ጀምሮ ህዝ ቤን ᵇለማዳን የተዘጋጀሁ እኔ ነኝ። እነሆ፣ እኔ ኢየሱስ ክርስቶስ ነኝ። እኔ ᵃአብም ወል ድም ነኝ። በእኔም የሰው ዘር በሙሉ፣ እን ዲሁም በስሜም የሚያምኑትም፣ የዘለዓለም ᶜህይወትን ያገኛሉ፤ እናም እነርሱም ᵐወን ድና ሴት ልጆቼም ይሆናሉ።

፲፭ እናም እኔ ለፈጠርኩት ሰው በጭራሽ ራሴን አላሳየሁም፤ ምክንያቱም ማንም አንተ እንዳደረግኸው በእኔ ᵇያመነ አልነ በረምና። አንተ በእኔ ᵃአምሳል መፈጠር ህን ተመልክተሃልን? አዎን፣ ሰዎች ሁሉ እንኳ በመጀመሪያ የተፈጠሩት በእኔ አም ሳል ነው።

፲፮ እነሆ፣ ይህ ሰውነት፣ አሁን የተመለከ ትከው፣ ᵇመንፈሳዊው ሰውነቴ ነው፤ እናም ሰውን የፈጠርኩት በመንፈስ አካሌ አምሳል ነው፤ እናም በመንፈስ ለአንተ እንደታየ ሁት ለህዝቤም በሥጋ እታያለሁ።

፲፯ እናም እንግዲህ እንዳልኩት እኔ ሞሮኒ ስለተፃፉት ስለነዚህ ነገሮች ሙሉ ታሪክን መፃፍ አልችልም፤ ስለዚህ ኢየሱስ ለኔፋ ውያን እራሱን እንዳሳየው በዚሁ መልክ ለዚህ ሰው ᵇራሱን በመንፈስ አሳይቷል ማለቱ ይበቃኛል።

፲፰ እናም እርሱም ለኔፋውያን እንዳስተ ማራቸው አስተምሮታል፤ እናም ይህን ሁሉ ያደረገው ጌታ ብዙ ታላላቅ ስራዎችን ባሳ የው ምክንያት ይህ ሰው አምላክ መሆኑን ያውቅ ዘንድ ነው።

፲፱ እናም ይህ ሰው ከነበረው እውቀትም የተነሳ ᵇበመጋረጃው ውስጥ ከመመልከት ሊጠበቅ አልቻለም፤ እናም የኢየሱስን ጣት ተመለከተ፤ በተመለከተም ጊዜ በፍርሃት ወደቀ፤ ምክንያቱም የጌታ ጣት መሆኑን አውቋልና፤ እናም እንግዲህ እምነት የለ ውም፣ ምክንያቱም ምንም ባለመጠራጠር ያውቃለና።

፯ *ለ* ኤተር ፲፪፡ ፲፱፣ ፳፩።
፱ *ሀ* ቅ.መ.መ. ስጋ፣ ስጋዊ፣ የሚሞት፣ ኢየሱስ ክርስቶስ።
፲፪ *ሀ* ዕብ. ፮፡ ፲፰።
፲፫ *ሀ* ት. እና ቃ. ፳፯፡ ፲–፲፩።
ለ ኢኖስ ፩፡ ፮–፰።
ሐ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—የክርስቶስ ቅድመ ምድራዊ ህይወት።
፲፬ *ሀ* ቅ.መ.መ. መድኃኒት፣ ቤዛ፣ ማዳን፣ ቤዛነት።
ለ ሞዛያ ፲፭፡ ፩–፬።
ሐ ሞዛያ ፲፮፡ ፱።
መ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ወንድ እና ሴት ልጆች።
፲፭ *ሀ* ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
ለ ዘፍጥ. ፩፡ ፳፯–፳፯፣ ሞዛያ ፯፡ ፳፯፣ ት. እና ቃ. ፳፡ ፲፯–፲፰።
፲፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. መንፈስ።
፲፯ *ሀ* ቮ ኔፊ ፲፩፡ ፳–፲።
፲፱ *ሀ* ቅ.መ.መ. ዐይኑ-እርግብ።

፳ ስለዚህ፣ ይህን የእግዚአብሔር ፍፁም የሆነ እውቀት ስላለው፣ በመጋረጃው ውስጥ ሊጠበቅ ᵐአልተቻለውም፤ ስለዚህ ኢየሱስን ተመለከተው፤ እናም እርሱም አስተማረው።

፳፩ እናም እንዲህ ሆነ ጌታ የያሬድን ወንድም እንዲህ አለው፡ እነሆ፣ ስሜን በᵐጋ ሆኜ ለማስከበር ᵐእስከምመጣበት ጊዜ ድረስ እነዚህ ያየሃቸውን እናም የሰማሃቸውን ነገሮች ወደዓለም እንዲሄዱ አትፍቀድ፤ ስለዚህ፣ ያየሃቸውን እናም የሰማሃቸውን ነገሮች አስቀምጥ፣ እናም ለማንም አታሳይ።

፳፪ እናም እነሆ፣ ወደ እኔ በምትመጣበት ጊዜም ፃፈው፣ እናም ማንም ሊተረጉማቸው እንዳይችልም አሽገው፤ ምክንያቱም ለማንበብ በማይቻል ቋንቋ ትጽፋቸዋለህና።

፳፫ እናም እነሆ፣ እነዚህን ᵐሁለት ድንጋዮች እሰጥሃለሁ፣ እናም ደግሞ ከምትጽፋቸው ነገሮች ጋር ትቀብራቸዋለህ።

፳፬ እነሆም የምትጽፈው ቋንቋ አምታትቼዋለሁ፤ ስለዚህ አንተ የምትፅፋቸውን ነገሮች በራሴ ጊዜም እነዚህ ድንጋዮች ለሰዎች አይኖች እንዲያደምቋቸው አደርጋለሁ።

፳፭ እናም ጌታም እነዚህን ቃላት በተናገረ ጊዜ፣ ለያሬድ ወንድም የምድር ᵐፍጡር የሆኑትን ሁሉ፣ እናም ደግሞ ሊሆኑ የሚችሉትን በሙሉ አሳየው፤ እናም እስከምድር ዳርቻም ከያሬድ ወንድም ፊት አልደበቀውም።

፳፮ ከዚህ በፊትም በእርሱ ᵐየሚያምን ᶮከሆነ ሁሉንም ነገሮች ሊያሳየው እንደሚችል ተናግሮታልና—ለእርሱም ያሳየዋል፤ ስለዚህ ጌታ ከእርሱ ሊደብቅ የሚቻለው ምንም ነገር የለም፤ ምክንያቱም ጌታ ᵒሁሉንም ነገሮች ሊያሳየው እንደሚችል ያውቃልና።

፳፯ እናም ጌታ እንዲህ አለው፡ እነዚህን ነገሮች ፃፍ፣ እናም ᵐአትማቸው፣ እናም የራሴ ጊዜ ሲደርስ ለሰው ልጆች አሳያቸዋለሁ።

፳፰ እናም እንዲህ ሆነ ጌታም የተቀበላቸውን ሁለት ᵐድንጋዮች እንዲያሽጋቸው እናም ጌታም ለሰው ልጆች እስከሚያሳያቸው እርሱ ለማንም እንዳያሳያቸው አዘዘው።

ምዕራፍ ፬

ሞሮኒ የያሬድን ወንድም ጽሑፎች እንዲያሽጋቸው ታዘዘ—ጽሑፎቹም ሰዎች እንደያሬድ ወንድም እምነት እስከሚኖራቸው አይገለፁም—ክርስቶስም ሰዎች ቃሉን እናም የደቀመዛሙርቱን ቃላት እንዲያምኑ አዘዛቸው—ሰዎች ንሰሃ እንዲገቡ፣ ወንጌልን እንዲያምኑ፣ እና እንዲድኑ ታዘዋል።

፩ እናም ጌታም የያሬድን ወንድም ጌታ ካለበት ተራራ ወርዶ እንዲመጣ፣ እናም ያያቸውን ነገሮች ᵐእንዲፅፍ አዘዘው፤ እርሱም በመስቀል ላይ ᶮእስከሚሰቀል ወደ ሰው ልጆች እንዳይመጡ ተከልክለዋል፤ እናም በዚህም የተነሳ ክርስቶስ ለህዝቡ እራሱን እስኪገልፅ ወደ ዓለም መምጣት ስለሌለባቸው ንጉስ ሞዛያ ጠበቃቸው።

፪ እናም ክርስቶስም በእውነት እራሱን ለህዝቡ ከገለፀ በኋላ ጽሑፎቹ እንዲገለጡ አዘዘ።

፫ እናም፣ እንግዲህ፣ ከዚያን በኋላ፣ ሁሉም እምነት አጥተው መነመኑ፤ እናም ከላማናውያን በስተቀር ማንም አልነበረም፣ እናም እነርሱም የክርስቶስን ወንጌል አስወግደዋል፤ ስለዚህ እኔ በድጋሚ ጽሑፎችን በመሬት ውስጥ ᵐእንድደብቅ ታዘዝኩ።

፬ እነሆ፣ በእነዚህ ሰሌዳዎች ላይ የያሬድ ወንድም የተመለከታቸውን ነገሮችን ፅፌ

፳ ሀ ኤተር ፲፪፡ ፲፱–፳፩።
፳፩ ሀ ኤተር ፬፡ ፩።
፳፫ ሀ ቅ.መ.መ. ኡሪም እና ቱሚም።
፳፭ ሀ ሙሴ ፩፡ ፳።
፳፮ ሀ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
ለ ኤተር ፫፡ ፲፩–፲፫።
ሐ ኤተር ፬፡ ፬።
፳፯ ሀ ፪ ኔፊ ፳፯፡ ፯–፳።
፳፰ ሀ ት. እና ቃ. ፲፯፡ ፩።
፬ ፩ ሀ ኤተር ፲፪፡ ፳፬።
ቅ.መ.መ. ቅዱሳት መጻህፍት።
ለ ኤተር ፫፡ ፳፩።
፫ ሀ ሞር. ፳፡ ፲፬።

አለሁ፤ እናም ለያሬድ ወንድም ከተገለፀው በላይ የተገለፁ ታላቅ የሆኑ ነገሮች በጭራሽ አልነበሩም።

፭ ስለዚህ ጌታም እንድፅፋቸው አዞኛል፤ እናም ፅፌአቸዋለሁ። እናም [ሀ]እንዳሽጋቸው አዞኛል፤ እናም ደግሞ ትርጉሙን እንዳሽግ አዞኛል፤ እናም በጌታም ትዕዛዝ በመመራት [ለ]ተርጓሚዎቹን አሽግኋቸው።

፮ ጌታም እንዲህ ብሎኛልና፥ አህዛብ ለክፋቶቻቸው ንስሃ እስከሚገቡበት ቀን እናም በጌታም ፊት ንፁህ እስከሚሆኑ ድረስ ወደ እነርሱ አይሄዱም።

፯ እናም ጌታም እንዲህ አለ፥ በእኔ [ሀ]እንዲነጹ ዘንድ፣ በዚያን ቀንም የያሬድ ወንድም እንዳደረገው በእኔ ታማኝ ይሁኑ፤ ከዚያም በኋላ እኔም የያሬድ ወንድም የተመለከታቸውን ነገሮች፣ እንዲሁም ራዕዮቼን በሙሉ እገልፅላቸዋለሁ ይላል የሰማይና የምድር [ለ]አባት፣ እናም በእነርሱ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ነገሮች የፈጠረ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ።

፰ እናም ከጌታ ቃል ጋር [ሀ]የሚከራከር፣ የተረገመ ይሁን፤ እናም እነዚህን ነገሮች [ለ]የሚክድ፣ የተረገመ ይሁን፤ [ሐ]ምንም ታላቅ ነገሮችን ለእነርሱ አላሳያቸውም፣ ይላል ኢየሱስ ክርስቶስ፤ የምናገራችሁም እኔ ነኝና።

፱ እናም በእኔ ትዕዛዝ ሰማያት ይከፈታሉ እንዲሁም [ሀ]ይዘጋሉ፤ በቃሌም [ለ]ምድር ትንቀጠቀጣለች፤ እናም በትዕዛዜ ነዋሪዎችዋ በእሳትም እንኳን ቢሆን ይጠፋሉ።

፲ እናም ቃላቴን የማያምን ደቀመዛሙርቶቼንም አያምንም፤ እናም ይህን የማልናገር ከሆነ እናንተ ፍረዱ፤ ምክንያቱም [ሀ]በመጨረሻው ቀን እኔ እንደምናገር ታውቃላችሁና።

፲፩ ነገር ግን እኔ የተናገርኳቸውን እነዚህን ነገሮች [ሀ]የሚያምን በመንፈሴ መገለጥ እጎበኘዋለሁ፤ እናም እርሱ ያውቃል እናም ይመሰክራል። ምክንያቱም በመንፈሴ እነዚህ ነገሮች [ለ]እውን መሆናቸውን [ሐ]ያውቃል፤ ሰዎች መልካም እንዲሰሩም ይገፋፋቸዋልና።

፲፪ እናም ሰዎች መልካምን ነገር እንዲሰሩ የሚገፋፋ ከእኔ የሆነ ነው፤ ከእኔ ካል ሆነ በቀር [ሀ]መልካም የሆነ ከማንም አይመጣምና። እኔ ሰዎችን መልካም ወደሆነው ሁሉ የምመራ ነኝ፤ ቃሌን [ለ]የማያምን በእኔ አያምንም—እኔም እንደሆንኩኝ አያምንም፣ እናም በእኔ የማያምን በላከኝ በአብ አያምንም። እነሆም፣ እኔ [ሐ]አባት ነኝ፤ የዓለምም ብርሃን፣ [መ]ህይወትም፣ እውነትም ነኝ።

፲፫ አህዛብ ሆይ ወደ እኔ [ሀ]ኑ፣ እናም ታላቅ የሆኑትን ነገሮች፣ ባለማመንም የተደበቁትን እውቀቶች እንድታውቁ አሳያችኋለሁ።

፲፬ እናንተ የእስራኤል ቤት ሆይ፣ ወደ እኔ ኑ፤ እናም አብ ከዓለም መፈጠር ጀምሮ ምን ያህል ታላቅ ነገሮችን እንዳዘጋጀላችሁ [ሀ]ይገለፅላችኋል፤ እናም እናንተ ባለማመናችሁ ምክንያት ሊደርሱ አልቻሉም።

፲፭ እነሆ፣ በክፋታችሁ በአሰቃቂ ሁኔታ እንድትቀሩ እናም በልባችሁ ጠጣርነት እናም በአእምሮአችሁ መታወር እንድትቀሩ የሚያደርጋችሁን የአለማመን መጋረጃ ስትቀዱት፣ ከዓለም መፈጠር ጀምሮ ታላቁ እና አስደናቂው ነገር ከእናንተ [ሀ]የተደበቀው—አዎን፣ በተሰበረ ልብ እና በተዋ

፭ ሀ ኤተር ፭፥ ፩።
ለ ት. እና ቃ. ፲፯፥ ፩፤ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥ ፶፪። ቅ.መ.መ. ኡሪም እና ቱሚም።
፯ ሀ ቅ.መ.መ. ቅድስና።
ለ ሞዛያ ፫፥ ፰።
፰ ሀ ፫ ኔፊ ፳፱፥ ፭–፯፤ ሞር. ፰፥ ፲፯።
ለ ፪ ኔፊ ፳፯፥ ፲፬፤ ፳፰፥ ፳፱–፴።
ሐ አልማ ፲፪፥ ፲–፲፩፤ ፫ ኔፊ ፳፮፥ ፱–፲።
፱ ሀ ፩ ነገሥ. ፰፥ ፴፭፤ ት. እና ቃ. ፸፯፥ ፰።
ለ ሔለ. ፲፪፥ ፰–፲፰፤ ሞር. ፭፥ ፳፫።
፲ ሀ ፪ ኔፊ ፴፫፥ ፲–፲፭።
፲፩ ሀ ት. እና ቃ. ፭፥ ፲፮።
ለ ኤተር ፭፥ ፫–፬፤ ሞሮኒ ፲፥ ፬–፭።
ሐ ቅ.መ.መ. ምስክርነት።
፲፪ ሀ አልማ ፭፥ ፵፤ ሞሮኒ ፯፥ ፲፮–፲፯።
ለ ፫ ኔፊ ፳፰፥ ፴፬።
ሐ ቅ.መ.መ. ብርሀን፣ የክርስቶስ ብርሀን።
መ ዮሐ. ፰፥ ፲፪፤ አልማ ፴፰፥ ፱።
፲፫ ሀ ፫ ኔፊ ፲፪፥ ፪–፫።
፲፬ ሀ ት. እና ቃ. ፻፳፩፥ ፳፮–፳፱።
፲፭ ሀ ፪ ኔፊ ፳፯፥ ፲።

ረደ መንፈስ፣ አብን በስሜ ስትጠሩት፣ አብ
ለአባቶቻችሁ፣ አቤቱ ለእስራኤል ቤት፣
የገባውን ቃል ኪዳን እንደሚያስታውስ
ታውቃላችሁ።
፲፮ እናም በአገልጋዬ በዮሐንስ እንዲፃፉ
ያደረግኋቸው [ሀ]ራዕዮቼ በሰዎች ሁሉ ፊት
ይከፈታሉ። እነዚህን ነገሮች በምትመለ
ከቱበት ጊዜ በእርግጥ ስራ የሚገለጡበት
ጊዜ መቃረቡን ማወቃችሁን አስታውሱ።
፲፯ ስለዚህ፣ ይህንን መዝገብ [ሀ]በምትቀበ
ሉበት ጊዜ የአብ ሥራ በምድር ላይ መጀ
መሩን ታውቃላችሁ።
፲፰ ስለዚህ፣ እስከምድር ዳርቻ ያላ
ችሁ ሁሉ [ሀ]ንሰሃ ግቡ፣ እናም ወደ እኔም
ኑ፣ እናም ወንጌሌን እመኑ፣ እናም በስሜ
[ለ]ተጠመቁ፤ ያመነ እናም የተጠመቀ ይድ
ናልና፤ ያላመነ ግን ይኮነናል፤ እናም በስሜ
የሚያምኑትን [ሐ]ምልክቶች ይከተሏቸዋል።
፲፱ እናም በመጨረሻው ቀን ለስሜ
[ሀ]ታማኝ ሆኖ የሚገኝ የተባረከ ነው፤ ምክ
ንያቱም ከዓለም [ለ]መፈጠር ጀምሮ ለእርሱ
በተዘጋጀለት መንግስት ለመኖር እርሱ ከፍ
ይላልና። እናም እነሆ ይህን የምናገረው እኔ
ነኝ። አሜን።

ምዕራፍ ፭

ሦስቱ ምስክሮች እናም ስራው እራሱ የመፅሐፈ ሞርሞንን እውነተኛነት ለመመስክር ይቆማሉ።

፩ እናም እንግዲህ እኔ ሞሮኒ ባስታወስ
ኩኝ መጠን የታዘዝኳቸውን ቃላት ፅፌአ
ለሁ፤ እናም [ሀ]ያተምኳቸውን ነገሮች ነገር
ኳችሁ፤ ስለዚህ ትተረጉሟቸው ዘንድም
አትንኳቸው፤ ከጊዜ ወደ ጊዜም በእግዚ
አብሔር ጥበብ ካልሆነ በቀርም ተከልክ
ለዋልና።
፪ እናም እነሆ፣ ይህንን ሥራ ለማምጣት
[ሀ]ለሚረዱአችሁ ሰሌዳዎቹን ታሳዩአቸው
ዘንድ ዕድሉም ይኖራችኋል፤
፫ እናም በእግዚአብሔር ኃይልም
[ሀ]ለሦስቱ የሚታዩ ይሆናሉ፤ ስለዚህ እነ
ዚህ ነገሮች [ለ]እውነት መሆናቸውን በእር
ግጥ [ሐ]ያውቃሉ።
፬ እናም በሦስት ሰዎች አንደበት፣ እናም
በሦስቱ [ሀ]ምስክርነት እናም የእግዚአብ
ሔር ኃይል በሚታይበት በዚህ ሥራ፣
እናም ደግሞ በአብ እናም በወልድ፣ እናም
በመንፈስ ቅዱስ በሚመሰከርበት ቃል እነ
ዚህ ነገሮች ይፀናሉ፤ እናም በመጨረሻው
ቀንም ይህ ሁሉ በዓለም ላይ ለምስክርነት
ይቆማል።
፭ እናም እነርሱ ንሰሃ ቢገቡ፣ እናም በኢ
የሱስ ስም ወደ አብ [ሀ]ቢመለሱ፤ በእግዚአ
ብሔር መንግስትም ተቀባይነትን ያገኛሉ።
፮ እናም እንግዲህ፣ በእነዚህ ነገሮች ላይ
ስልጣን ከሌለኝ እናንተ ፍረዱብኝ፤ ምክን
ያቱም እኔን ስትመለከቱኝ ስልጣን እንዳለኝ
ታውቃላችሁና፣ እናም በመጨረሻው ቀን
በእግዚአብሔር ፊት እንቆማለን። አሜን።

ምዕራፍ ፮

የያሬዳውያን ጀልባዎች በነፋሱ ወደ ቃል ኪዳን ምድር ተወሰዱ—ህዝቡም ጌታ ቻር በመሆኑ አወደሱት—ኦሪያም በእነ

፲፮ ሀ ራዕ. ፩፥፩፤
፩ ኔፊ ፲፬፥፲፰–፳፯።
፲፯ ሀ ፫ ኔፊ ፳፩፥፩–፱፣ ፳፰።
፲፰ ሀ ፫ ኔፊ ፳፯፥፳፤
ሞሮኒ ፯፥፴፬።
ለ ዮሐ. ፫፥፫–፭።
ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣
መጥመቅ—አስፈላጊ።
ሐ ቅ.መ.መ. የመንፈስ
ስጦታዎች።
፲፱ ሀ ሞዛያ ፪፥፵፩፤
ት. እና ቃ. ፯፥፲፫።
ቅ.መ.መ. ኢየሱስ
ክርስቶስ—የክርስቶስን ስም
በራሳችን ላይ መውሰድ።
ለ ፪ ኔፊ ፱፥፲፰።
፭ ፩ ሀ ፪ ኔፊ ፳፯፥፯–፰፣ ፳፩፤
ኤተር ፬፥፬–፯።
፪ ሀ ፪ ኔፊ ፳፯፥፲፪–፲፬፤
ት. እና ቃ. ፭፥፱–፲፭።
፫ ሀ ፪ ኔፊ ፲፩፥፫፤ ፳፯፥፲፪።
ለ ኤተር ፬፥፲፩።
ሐ ት. እና ቃ. ፭፥፳፭።
፬ ሀ የት. እና ቃ. ፲፯ ርዕስን እና
ቁጥር ፩–፫ን ተመልከቱ፤
ደግሞም በመፅሐፈ ሞርሞን
የመጀመሪያ ገጾች ውስጥ
“የሶስቱ ምስክሮች
ምስክርነት” ተመልከቱ።
፭ ሀ ሞር. ፱፥፳፯፤
ሞሮኒ ፲፥፴–፴፪።

ርሱ ላይ ንጉስ እንዲሆን ተሾመ—ያሬ ድና ወንድሙ ሞቱ።

፩ እናም እንግዲህ፣ እኔ ሞሮኒ፣ የያሬድን እና የወንድሙን ዘገባ መስጠቴን እቀጥላ ለሁ።

፪ እናም እንዲህ ሆነ የያሬድ ወንድም ወደ ተራራው ተሸክሞ የወሰዳቸውን [a]ድንጋዮች ጌታ ካዘጋጃቸው በኋላ፣ የያሬድ ወንድም ከተራራው ላይ ወረደ፣ እናም ድንጋዮቹን በጀልባዎች ውስጥ እያንዳንዱን በጫፉ ላይ አስቀመጠው፤ እናም እነሆ፣ ድንጋዮቹም ለመርከቡ ብርሃን ሰጡ።

፫ እናም ታላቁንም ውሃ በጨለማ እን ዳያቋርጡ ዘንድ ጌታ ድንጋዮቹን ለወን ዶች፣ ለሴቶች እና ለህፃናት ብርሃን እንዲ ሰጡ በጨለማም እንዲያበሩ አደረገ።

፬ በውኃ ላይ በሚቆዩበት ጊዜ የሚኖሩበት የተለያዩ የምግብ ዓይነቶችን አዘጋጅተው ነበር፣ እናም ደግሞ ለበጎቻቸው፣ እናም ለመንጋዎቻቸው፣ እናም ለያዙአቸው አራ ዊቶች ወይም እንስሳቶች፣ ወይም ወፎች ሁሉ ምግብ ይዘው ነበር—እናም እንዲህ ሆነ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ካደረጉ በኋላ፣ እራሳቸውን ለጌታ ጥበቃ አሳልፈው በመስ ጠት፣ ወደ ውሀ መጓዣቸው ወይም በጀል ባዎቻቸው ሄዱ።

፭ እናም እንዲህ ሆነ ጌታ እግዚአብሔ ርም ወደ ቃል ኪዳኗ ምድር በሚያመራው በውኃው ገፅ ላይ [b]ኃይለኛ ነፋስ እንዲነ ፍስ አደረገ፤ እናም ከነፋሱም በፊት በባህሩ ሞገድ ተወስደው ነበር።

፮ እናም እንዲህ ሆነ በእነርሱ ላይ ባረፈው በተራራማው ማዕበል እናም ደግሞ በኃያሉ ነፋስ ምክንያት በመጣው በታላቁና ኃይለ ኛው አውሎ ነፋስ ብዙ ጊዜ ባህሩ ውስጥ ተቀብረው ነበር።

፯ እናም እንዲህ ሆነ ጀልባዎቻቸው እን ደማህን [c]የጠበቀ ስለነበሩ፣ እናም ደግሞ እንደኖህ [d]መርከብም የጠበቁ ስለነበሩ፣ ወደ ጥልቅ ውሀውም በሚቀበሩበትም ጊዜ የሚጎዳቸው ውኃ አልነበረም፤ ስለዚህ በበ ርካታ ውኃም በተከበቡም ጊዜ ወደ ጌታ ጮሁ እናም እርሱም በድጋሚ ከብዙ ውሀ ዎች በላይ አወጣቸው።

፰ እናም እንዲህ ሆነ እነርሱም በውኃው ላይ በነበሩበት ጊዜ ነፋሱ ወደ ቃል ኪዳኗ ምድር መንፈሱን በጭራሽ አላቆመም፤ እናም ከነፋሱ በፊትም እንደዚህ ተገፉ።

፱ እናም ጌታን [e]በዝማሬ ያወድሱት ነበር፤ አዎን፣ የያሬድ ወንድም ጌታን በዝማሬ ያወድሰው ነበር፣ እናም ቀኑን ሙሉ ጌታን [f]ያመሰግነው እናም ያወድሰው ነበር፤ እናም ምሽት በሆነም ጊዜ ጌታን ማወደሳቸውን አላቆሙም ነበር።

፲ እናም በዚሁ ወደ ፊት ሄዱ፤ እናም ምንም የባህር አውሬም ሊሰብራቸው አል ቻለም፣ አሳ ነባሪም ሊጎዳቸው አልቻ ለም፤ እናም በውኃው ከላይ በኩል እንዲ ሁም ከታችም ቢሆኑም ያለማቋረጥ ብር ሃን ነበራቸው።

፲፩ እናም ለሦስት መቶ አርባ አራት ቀናት በውኃው ላይ ይጓዙ ነበር።

፲፪ እናም በቃል ኪዳኗ ምድር ዳርቻም አረፉ። እናም በቃል ኪዳኗ ምድር እግራ ቸውን ባሳረፉ ጊዜ በምድሪቷ ላይ እራሳቸ ውን ዝቅ አደረጉ፣ እናም በጌታ ፊት እራ ሳቸውን አዋረዱ፣ እና ጌታም በእነርሱ ላይ ምህረቱን ያበዛ በመሆኑ በፊቱ የደስታ እን ባቸውን አፈሰሱ።

፲፫ እናም እንዲህ ሆነ በምድሪቱም ላይ ተሰራጩ እናም እርሻ ጀመሩ።

፲፬ እናም ያሬድ አራት ወንዶች ልጆች ነበሩት፤ እናም እነርሱም ያቆም፤ እናም ጊልጋ፣ እናም ማሃ እናም ኦሪያ ተብለው ይጠሩ ነበር።

፲፭ እናም ደግሞ የያሬድ ወንድም ወን ድና ሴት ልጆችን ወለደ።

፮ ፪ *ሀ* ኤተር ፫፡፫–፮።
፭ *ሀ* ኤተር ፪፡ ፳፩–፳፭።
፯ *ሀ* ኤተር ፪፡ ፲፯።
ለ ዘፍጥ. ፮፡ ፲፩፤ ሙሴ ፯፡ ፳፫።
፱ *ሀ* ቅ.መ.መ. መዘመር።
ለ ፩ ዜና ፲፯፡ ፯–፱፤ አልማ ፴፯፡ ፴፯፤ ት. እና ቃ. ፵፯፡ ፴፪።

፲፮ እናም የያሬድ [ሀ]ወዳጆች እናም ወንድ ሞቹ በቁጥር ሃያ ሁለት ነፍሳት ነበሩ፤ እናም እነርሱ ደግሞ ወደ ቃልኪዳኗ ምድር ከመ ምጣታቸው በፊት ወንድና ሴት ልጆችን ወልደው ነበር፤ እናም ስለዚህ ብዙ መሆን ጀምረው ነበር።

፲፯ እናም እነርሱም በጌታ ፊት በትህትና [ሁ]መራመድን ተምረው ነበር፤ እናም ከላይ ከሰማይም ደግሞ [ሂ]ተምረው ነበር።

፲፰ እናም እንዲህ ሆነ በምድሪቱ ላይ መስፋፋት፣ እናም መባዛት፣ እናም ምድ ሪቷን ማረስ ጀመሩ፤ እናም በምድሪቱ ላይ ጠነከሩ።

፲፱ እናም የያሬድ ወንድም አረጀ፣ እናም በቅርቡም ወደ መቃብር መውረድ እንዳ ለበት ተመለከተ፤ ስለዚህ ለያሬድ እን ዲህ ሲል ተናገረው፡ ሕዝባችንን እንድ ንቆጥር፣ ወደ መቃብራችን ከመውረዳችን በፊት ከእኛ የሚፈልጉትን እናውቅ ዘንድ ህዝቦቻችንን በአንድነት እንሰብስባቸው።

፳ እናም በዚህም መሰረት ህዝቡም በአ ንድነት ተሰባስቦ ነበር። እንግዲህ የያሬድ ወንድም ወንዶችና ሴቶች ልጆቹ በቁ ጥር ሃያ ሁለት ነፍሳት ነበሩ፤ እናም የያ ሬድ ወንዶችና ሴቶች ልጆቹ አስራ ሁለት ነበሩ፤ እናም አራት ወንድ ልጆች ነበሩት።

፳፩ እናም እንዲህ ሆነ ያሬድና ወንድ ሙም ህዝባቸውን ቆጠሩ፤ እናም ከቆጠሩ አቸው በኋላም ወደ መቃብር ከመውረዳ ቸው በፊት ከእነርሱ የሚፈልጓቸውን ነገ ሮች ለማወቅ ፈለጉ።

፳፪ እናም እንዲህ ሆነ ህዝቡም የፈለጉት ከልጆቻቸው አንዱን በእነርሱ ላይ ንጉስ አድርገው [ሁ]እንዲቀቡት ነበር።

፳፫ እናም አሁን እነሆ፣ ይህ ለእነርሱ አሳዛኝ ነበር። እናም የያሬድ ወንድም እን ዲህ አላቸው፡ በእርግጥ ይህ ነገር ወደ ግዞት [ሂ]ያመራል።

፳፬ ነገር ግን ያሬድ ለወንድሙ እንዲህ አለው፡ ንጉስ ይኖራቸው ዘንድ ፍቀድ ላቸው። እናም ስለዚህ እንዲህ አላቸው፡ ከወንዶች ልጆቻችን እናንተም የፈለጋች ሁትን አንድን ንጉስ ምረጡ።

፳፭ እናም እንዲህ ሆነ የያሬድን ወንድም የበኩር ልጁን መረጡ፤ ስሙም ፓጋግ ይባል ነበር። እናም እንዲህ ሆነ እርሱም ንጉሳቸው መሆንን አልተቀበለውም፣ እናም ንጉሳቸው አልሆነም። እናም ህዝቡ አባቱ እንዲገፋፋው ፈለጉ፣ ነገር ግን አባቱ አላስገደደውም፤ እናም እርሱም ማንንም ሰው ንጉስ ሁን ብለው እንዳያስገድዱ አዘ ዛቸው።

፳፮ እናም እንዲህ ሆነ የፓጋግን ወንድ ሞች በሙሉ መረጡአቸው፣ እናም እነር ሱም ንጉስ ለመሆን አልፈለጉም።

፳፯ እናም እንዲህ ሆነ ከአንዱ በስተቀር የያሬድ ወንድም ልጆች ሁሉም አልፈለ ጉም፤ እናም ኦሪያ በህዝቡ ላይ ንጉስ ለመ ሆን ተቀብቶ ነበር።

፳፰ እናም እርሱ መንገስ ጀመረ፣ እናም ህዝቦቹ መበልፀግ ጀመሩ፤ እናም እጅግ ሀብታም ሆኑ።

፳፱ እናም እንዲህ ሆነ ያሬድ እንዲሁም ደግሞ ወንድሙም ሞቱ፤

፴ እናም እንዲህ ሆነ ኦሪያ በጌታ ፊት እራሱን ዝቅ አድርጎ ተራመደ፣ እናም ጌታም ለአባቱ ምን ያህል ድንቅ ነገሮችን እንዳደረገ አስታወሰ፤ እናም ደግሞ ጌታ ለአባቶቻቸው ምን ያህል ታላላቅ ነገሮችን እንዳደረገላቸው ለህዝቡ አስተማራቸው።

ምዕራፍ ፯

ኦሪያ በፅድቅ ነገሰ—ያለአግባብ ሥልጣ ንን በመያዝና በፀብ መካከል ተቃዋሚዎቹ የሾል እናም የቆሖር መንግስታት ተመ ሰረቱ—ነቢያት የህዝቡን ክፋትና ጣኦት አምላኪነት ኮነኑ፣ ከዚያም ንሰሃ ገቡ።

[ሀ] ኤተር ፩፡፴፩።
[ሁ] ቅ.መ.መ. መራመድ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መራመድ (መሄድ)።
[ሂ] ለ ቅ.መ.መ. ራዕይ።
[ሃ] ሀ ቅ.መ.መ. መቀባት።
[ሄ] ሀ ፩ ሳሙ. ፰፡፲–፲፰፣ ሞዛያ ፳፱፡፲፮–፳፫።

፩ እናም እንዲህ ሆነ ኦሪያ በዘመኑ ሁሉ በፅድቅ በምድሪቱ ላይ ፍርድን ፈፅሟል፤ ዘመኑም እጅግ ብዙ ነበር።

፪ እናም ወንዶች እና ሴቶች ልጆች ንም ወለደ፤ አዎን፣ ሠላሳ አንድ ልጆችን ወለደ፤ ከእነርሱ መካከል ሃያ ሦስቱ ወን ዶች ልጆች ነበሩ።

፫ እናም እንዲህ ሆነ እርሱም ደግሞ በእ ርጅናው ጊዜ ቂብን ወለደ። እናም እንዲህ ሆነ ቂብም በእርሱ ቦታ ነገሰ፤ እናም ቂብ ቆሪሆርን ወለደ።

፬ እናም ቆሪሆርም ሠላሳ ሁለት ዓመት በሞላው ጊዜ በአባቱ ላይ አመፀ፣ እናም ሄደ እናም በኔሆር ምድር ተቀመጠ፤ እናም እርሱም ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወለደ፣ እናም እነርሱም እጅግ ያማሩ ሆኑ፤ ስለ ዚህ ቆሪሆርንም ብዙ ሰዎች እንዲከተሉት ወደ እርሱ ሳቡ።

፭ እናም ሠራዊቱን በሰበሰበ ጊዜም ንጉሱ ወደሚኖርበት ወደ ሞሮን ምድር መጣ፣ እናም ምርኮኛ አድርገው ወሰዱት፣ ይህም የያሬድ ወንድም እነርሱ ምርኮኛ ይሆናሉ ᐟያለው ይፈፀም ዘንድ ሆነ።

፮ ንጉሱ የተቀመጠበት የሞሮን ምድር በኔፋውያን የወደመች ተብላ ከምትጠ ራው ምድር አጠገብ ነበረች።

፯ እናም እንዲህ ሆነ ቂብም በጣም እስከ ሚያረጅ ድረስ ቂብ እናም ህዝቡ በቆሪሆር በልጁ ስር በምርኮ ተቀምጠው ኖሩ፤ ይሁን እንጂ ቂብም በምርኮ በነበረበት ወቅት በእ ርጅናው ሹልን ወለደ።

፰ እናም እንዲህ ሆነ ሹልም በወንድሙ ተቆጥቶ ነበር፣ እናም ሹልም በረታ እናም በሰው ሀይልም ጠንክሮ ኃያል ሆነ፤ እናም በፍርዱም እንዲሁ ኃያል ነበር።

፱ ስለዚህ ወደ ኤፍሬም ኮረብታ ወጣ፣ እናም ከኮረብታው ብረት አቅልጦ አወጣ፣ እናም ከእርሱ ጋር ለሄዱትም ከብረቱ ጎራዴን ሰራላቸው፤ እናም በጎራዴም ካስ ታጠቃቸው በኋላ ወደ ኔሆር ከተማ ተመ ለሰ፣ እናም ከወንድሙ ቆሪሆር ጋር ተዋጋ፣ በዚህም መንገድ መንግስቱን አገኘ እናም ለአባቱ ቂብም መለሰለት።

፲ እናም እንግዲህ ሹል ባደረገው ነገር ምክንያት አባቱ መንግስቱን ለእርሱ ሰጠው፤ ስለዚህ በአባቱ ምትክም መንገስ ጀመረ።

፲፩ እናም እንዲህ ሆነ ሹልም በፅድቅ ፍር ድን ይፈጽም ነበር፤ እናም ህዝቡም በቁጥር እጅግ ብዙ በመሆናቸው በምድሪቱ ሁሉ ላይ አገዛዙን አስፋፋ።

፲፪ እናም እንዲህ ሆነ ሹልም ደግሞ ብዙ ወንዶችንና ሴቶች ልጆችን ወለደ።

፲፫ እናም ቆሪሆርም ለሰራቸው ብዙ ክፋ ቶች ንሰሃ ገባ፤ ስለዚህ ሹልም በመንግስቱ ሥልጣንን ሰጠው።

፲፬ እናም እንዲህ ሆነ ቆሪሆርም ብዙ ወንዶችና ሴቶች ልጆች ነበሩት። እናም ከቆሪሆር ወንድ ልጆች መካከልም አንዱ ኖህ የሚባል ነበር።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ ኖህም በንጉሱ በሹል፣ እናም ደግሞ በአባቱ ቆሪሆር ላይ አመፀ፤ ወንድሙ ቆሆርን፣ እናም ደግሞ ወንድሞቹን ሁሉ እናም ብዙ ሰዎችን ወደ ራሱ ሳበ።

፲፮ እናም ኖህም ከንጉሱ ሹል ጋር ተዋጋ፤ እናም በመጀመሪያ የትውልድ ቦታቸው የነ በረውን አገኘ፤ እናም በዚያም የምድሪቱ ክፍል ላይ ንጉስ ሆነ።

፲፯ እናም እንዲህ ሆነ በድጋሚም ከን ጉሱ ከሹል ጋር ተዋጋ፤ እናም ንጉስ ሹልን ወሰደ፣ እናም ወደ ሞሮን ምርኮኛ አድርጎ ወሰደው።

፲፰ እናም እንዲህ ሆነ ኖህም ሊገድ ለው በተዘጋጀ ጊዜ የሹል ልጆች በም ሽት አድፍጠው ወደ ኖህ ቤት ገብተው ገደሉት፣ እናም የወህኒ ቤቱን በር ሰበሩ እናም አባታቸውን አወጡት፣ እናም በራሱ መንግስትም በዙፋኑ ላይ መልሰው አስቀ መጡት።

፲፱ ስለዚህ፣ የኖህም ልጅ በእርሱ ምትክ መንግስቱን ገነባ፤ ይሁን እንጂ በንጉስ ሹል

ላይ ከዚያ በኋላ ኃይልን አላገኙም፤ እናም
በንጉስ ሹል አገዛዝ ሥር የነበሩ ሕዝቦች
እጅግ በለፀጉ እናም በኃይል ጠነከሩ።
፳ እናም ሀገሩም ተከፋፈለ፤ እናም ሁለት
መንግስት ነበሩ፣ የሹል መንግስት እናም
የኖህ ልጅ የሆነው የቆሆር መንግስት።
፳፩ እናም የኖህ ልጅ ቆሆር ህዝቡም
ከሹል ጋር እንዲዋጉ አደረገ፤ በዚያም
ሹልም ድልን አገኘ፣ እናም ቆሆርን ገደ
ለው።
፳፪ እናም እንግዲህ ቆሆርም ናምሩድ
የሚባል ልጅ ነበረው፤ እናም ናምሩድም
የቆሆርን መንግስት ለሹል ሰጠው፣ እናም
በሹል አመለካከትም ተወዳጅ ሆነ፤ ስለዚህ
ሹል ታላቅ ድጋፍን ሰጠው፤ እናም በሹል
መንግስት ውስጥ እንደ ፍላጎቱ አደረገ።
፳፫ እናም ደግሞ በሹል ንግስናም የህዝቡ
ክፋትና [ሀ]የጣዖት ማምለክ በምድሪቱ ላይ
እርግማን እንደሚያመጣ፤ እናም ህዝቡም
ንሰሃ ካልገባ እንደሚጠፉ የሚተነበዩ በህ
ዝቡ መካከል ከጌታ የተላኩ ነቢያት መጡ።
፳፬ እናም እንዲህ ሆነ ህዝቡም ነቢያትን
ሰደቡአቸው፣ እናም ተሳለቁባቸው። እናም
እንዲህ ሆነ ንጉስ ሹልም ነቢያቱን በተሳ
ደቡት ሁሉ ላይ ፍርድን ፈረደ።
፳፭ እናም በምድሪቱ ሁሉ ላይም በፈለ
ጉበት ቦታ ለመሄድ ለነቢያት ኃይልን ለመ
ስጠት ህጉ በስራ ላይ እንዲውል አደረገ፤
እናም በዚህም የተነሳ ህዝቡ ንሰሃ ገባ።
፳፮ እናም ህዝቡም ለክፋታቸው እና
ለጣዖት ማምለካቸው ንሰሃ በመግባታቸው
ጌታ አተረፋቸው፤ እናም በድጋሚ በምድ
ሪቱ ላይ መበልጸግ ጀመሩ። እናም እንዲህ
ሆነ ሹልም በእርጅናው ሴቶች እናም ወን
ዶች ልጆችን ወለደ።
፳፯ እናም በሹል ዘመን ምንም አይ
ነት ተጨማሪ ጦርነት አልነበረም፤ እናም
ጌታም ወደ ቃል ኪዳኗ ምድር ጥልቅ የነበ
ረውን ታላቅ ባህር [ሁ]በማሳለፍ ለአባቶቹ ያደ
ረገውን ታላቅ ነገር አስታወሰ፤ ስለዚህ በዘ
መኑ ሁሉ በፅድቅ ፍርድን አከናወነ።

ምዕራፍ ፳

በመንግስቱም ላይ ጥል እና ፀብ ሆነ—አኪሽ ንጉሱን ለመግደል በመሀላ የተሳሰረ ሚስጢራዊው ሴራ ሰራ—ሚስጢራዊው ሴራዎች የዲያብሎስ ናቸው እናም ሀገሪቱ ንም የማጥፋት ውጤት አላቸው—የዘመኑ አህዛቦችም የምድሮችን፣ የህዝቦችን፣ እና የሃገሮችን ሁሉ ነፃነት ለመገልበጥ ወደሚ ፈልገው ሚስጢራዊ ሴራ እንዳይገቡ ማስ ጠንቀቂያ ተሰጥቶአቸዋል።

፩ እናም እንዲህ ሆነ እርሱም ኦመርን
ወለደ፤ ኦመርም በእርሱ ምትክ ነገሰ።
እናም ኦመር ያሬድን ወለደ፤ እናም ያሬድ
ወንድ እና ሴት ልጆችን ወለደ።
፪ እናም ያሬድ በአባቱ ላይ አመፀ፣ እናም
ሔደ እናም በሔት ምድር ኖረ። እናም እን
ዲህ ሆነ የመንግስቱን ግማሽ እስከሚያገኝ
ድረስ በአጭበርባሪ ቃላቶቹ ብዙ ሰዎችን
ሸነገላቸው።
፫ እናም የመንግስቱን ግማሽ ባገኘ ጊዜ
ከአባቱ ጋር ተዋጋ፣ እናም አባቱን በም
ርኮ ወሰደው፣ እናም በምርኮም እንዲያገ
ለግል አደረገው፤
፬ እናም እንግዲህ፣ ኦመር በነገሰበት
ጊዜ ዘመኑን አጋማሽ በምርኮ ላይ ነበር።
እናም እንዲህ ሆነ ወንዶችና ሴቶች ልጆ
ችን ወለደ፤ ከእነርሱ መካከልም ኤስረምና
ቆሪያንተመር ነበሩ፤
፭ እናም በወንድማቸው በያሬድ ሥራ
ዎች እጅግ ተቆጥተው ነበር፤ በዚህም የተ
ነሳ ወታደሮችን አዘጋጁ እናም ከያሬድ ጋር
ተዋጉ። እናም እንዲህ ሆነ ከእርሱም ጋር
በምሽት ተዋጉ።
፮ እናም እንዲህ ሆነ የያሬድን ወታደሮች
በገደሉአቸው ጊዜ እርሱንም ለመግደል
ተቃርበው ነበር፤ እናም እርሱም እንዳይ
ገድሉት፣ እናም መንግስቱንም ትቶ ለአባቱ
እንደሚሰጥ ተማፀናቸው። እናም እንዲህ
ሆነ እነርሱም ህይወቱ እንዲተርፍ አደረጉ።
፯ እናም እንግዲህ ያሬድም መንግስ

[ሀ] ሆ ቅ.መ.መ. ጣኦት አምላኪ።
[ሁ] ሆ ኤተር ፮፡፱፣ ፲፪።

ቱን ስላጣ እጅግ አዘነ፣ ምክንያቱም እርሱ ልቡን በመንግስቱ ላይ እናም በዓለም ክብር ላይ አድርጎ ነበርና።

፰ እንግዲህ የያሬድ ሴት ልጅ ብልጥ ነበረች፣ እናም የአባቷን ሃዘንም ተመልክታ የአባቷን መንግስት ማዳን የምትችልበትን ዕቅድ ለመቀየስ አሰበች።

፱ እንግዲህ የያሬድ ሴት ልጅም እጅግ መልከ መልካም ነበረች። እናም እንዲህ ሆነ ለአባቷም እንዲህ ስትል ተናገረችው፡ በምን ምክንያት ነው አባቴ በኃይል ያዘ ነው? አባቶቻችን ታላቁን ጥልቅ አቋርጠው ያመጧቸውን መዛግብት አላነበባቸውምን? እነሆ፣ [a]በሚስጢራዊው ዕቅዳቸው መን ግስታቸውን እናም ታላቁን ክብራቸውን እንዳገኙ የሚናገር የጥንቶቹን በተመለከተ ታሪክ የለምን?

፲ እናም እንግዲህ፣ ስለዚህ አባቴም አኪሽ የቂምኖርን ልጅ ይጥራ፤ እናም እነሆ፤ እኔ ቆንጆ ነኝ፣ እናም በፊቱም [b]እወዛወዛለሁ፣ እናም አስደስተዋለሁ፣ ስለዚህ ለሚስትነት ይፈልገኛል፤ ስለዚህ እኔን ለሚስትነት እን ድትሰጠው ይፈልግሀል፣ ከዚያም እንዲህ በለው፡ የንጉሱን የአባቴን ራስ የምታመ ጣልኝ ከሆነ እርሷን እሰጥሃለሁ።

፲፩ እናም እንግዲህ ኦመር ለአኪሽ ወዳጅ ነበር፤ ስለዚህ ያሬድ አኪሽን በጠራው ጊዜ የያሬድ ሴት ልጅ በፊቱ ተወዛወዘች እናም አስደሰተችው፣ በዚህም የተነሳ ለሚስትነት ፈለጋት። እናም እንዲህ ሆነ ለያሬድም እን ዲህ አለው፡ እርሷን ለሚስትነት ስጠኝ።

፲፪ እናም ያሬድ እንዲህ አለው፡ የንጉሱን የአባቴን ራስ የምታመጣልኝ ከሆነ እርሷን እሰጥሃለሁ።

፲፫ እናም እንዲህ ሆነ አኪሽ በያሬድ ቤት ዘመዶቹን በሙሉ ሰበሰባቸው፤ እናም እን ዲህ ሲል ተናገራቸው፡ እኔ በምፈልግባ ችሁ ነገር ለእኔ ታማኝ ለመሆን ትምሉልኛ ላችሁን?

፲፬ እናም እንዲህ ሆነ አኪሽ ከፈለገው እርዳታ የተለየን የሚፈልግ ራሱን እንዲ ያጣ፣ እነርሱ ሁሉም በሰማይ አምላክ፣ እናም ደግሞ በሰማያት፣ እናም ደግሞ በም ድር እናም በህይወታቸው [c]መሃላን አደ ረጉ፤ እናም አኪሽ ለእነርሱ ያሳወቀውን ማንኛውን ነገር የሚገልፅ እርሱም ህይወ ቱን ያጣል።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ እነርሱም ከአኪሽ ጋር ተስማምተው ነበር። እናም አኪሽ በጥ ንት ጊዜ ሥልጣንን ይፈልጉ በነበሩት የተ ሰጣቸውን ከመጀመሪያው ገዳይ በነበረው [d]በቃየን የተላለፈውን [e]መሃላ እንዲገቡ አደ ረጋቸው።

፲፮ እናም እነርሱም ይህንን መሃላ ለህዝ ባቸው ለመስጠት፤ እነርሱንም በጨለማ ለማቆየት፤ ሥልጣንን ለማግኘት የሚፈል ጉትን ለመርዳት፤ እናም ለመግደል፣ እናም ለመዝረፍ፣ እናም ለመዋሸት፣ እናም ሁሉ ንም ዓይነት ክፋቶችን እና ዝሙት ለመፈ ፀም በዲያብሎስ ሃይል ተጠብቀው ነበር።

፲፯ እናም የጥንት የሆኑትን ነገሮች በሙሉ እንዲፈልግ ያደረገችው የያሬድ ሴት ልጅ ነበረች፤ እናም ያሬድ በአኪሽ ልብ ውስጥ ይህንን አስቀመጠ፣ ስለዚህ፣ አኪሽም ለነገ ዶቹ እናም ጓደኞቹም የፈለገውን ነገር እን ዲያደርጉለት መልካም በሆነ በተስፋ ቃል በመምራት መሃላን አስገባቸው።

፲፰ እናም እንዲህ ሆነ እነርሱም በጥንት ጊዜ እንደነበሩት [f]ሚስጢራዊ ሴራን አቋ ቋሙ፤ ህብረቱም በእግዚአብሔር ፊት ከሁሉም በላይ የከፋና የረከሰ ነው።

፲፱ ጌታም በሚስጢራዊ ሴራዎች አይ ሰራም፣ ወይም ሰዎችም ደም እንዲያፈሱ አይፈቅድም፣ ነገር ግን ከሰው መፈጠር ጀምሮ ይህንን ተግባር ከልክሏል።

፳ እናም እንግዲህ፣ እኔ ሞሮኒ፣ የመሃላ ውን አይነትም እንዲሁም ህብረቱን አል ፅፍም፣ ምክንያቱም እነርሱ በህዝቡ ሁሉ

---

[a] ፱ ሀ ሉሊ. ፤ ፡ ፳፯–፴፣ ፫ ኔፊ ፤ ፡ ፳፰፣ ሙሴ ፭ ፡ ፶፩–፶፪።

[b] ፱ ሀ ማር. ፤ ፡ ፳፪–፳፰።

[c] ፲ ሀ ቅ.መ.መ. መስደብ። ፲፭ ሀ ዘፍጥ. ፬ ፡ ፯–፰፣

[d] ሙሴ ፭ ፡ ፳፰–፴።

[e] ለ ቅ.መ.መ. መሀላ።

[f] ፲፰ ሀ ቅ.መ.መ. የሚስጥር ስብሰባ።

የነበሩ መሆናቸውን እንዳውቅ ተደርጌአለ ሁና፣ እናም በላማናውያንም መካከል አሉ።

፳፩ እናም አሁን እኔ ለምናገርላቸው ሰዎች እናም ደግሞ ለኔፊ ሕዝብ ᐸጥፋት ምክንያት ሆነዋል።

፳፪ እናም በሁሉም ሀገር እስከሚሰራጩ ድረስ፣ ሥልጣንን እናም ጥቅምን ለማግ ኘት እንደዚህ አይነቱን ሚስጢራዊ ሴራ ዎች የሚደግፍ ማንኛውም ሀገር፣ እነሆ ይጠፋል፤ ምክንያቱም ᐸደማቸው በእነ ርሱ የፈሰሰባቸው ቅዱሳንን በእነርሱ ላይ ᐹለበቀል ሁልጊዜም ከምድር እንዲጮኹ እናም ተመልሶም እንዳይበቀላቸው ጌታ አይፈቅድምና።

፳፫ ስለሆነም፣ አህዛብ ሆይ፣ ስለዚህ ለኃ ጢአቶቻችሁ ንሰሃ ትገቡ ዘንድ፣ እናም ᐸሥልጣንን እና ጥቅምን ለማግኘት የተሰ ሩት እነዚህ የግድያ ህብረቶችም ከእናንተ በላይ እንዲሆኑ እንዳትፈቅዱላቸው እነዚህ ነገሮች ለእናንተ መታየታቸው ለእግዚአ ብሔር ጥበብ ነው—እናም አዎን፣ እነዚህ ነገሮች እንዲሆኑም ከፈቀዳችሁ ሥራው አዎን፣ የጥፋት ሥራም በእናንተ ላይ ይሆ ናል፣ አዎን፣ የዘለዓለማዊው አምላክ የፍ ርድ ጎራዴ እናንተን ለመፈንቀል እና ለማ ጥፋት በላያችሁ ላይ ይወድቃል።

፳፬ ስለሆነም፣ በዚህ በእናንተ መካከል በመጣው ሚስጢራዊው ሴራ የተነሳ እነ ዚህን ነገሮች በእናንተ ላይ መምጣታቸ ውን በምትመለከቱበት ጊዜ፣ ስለአሰቃቂ ሁኔታችሁ ስሜታችሁን እንድታነቁ ዘንድ ጌታ ያዛችኋል፤ ወይም በተገደሉት ደማች ውም መፍሰስም የተነሳ ወዮላቸው፤ ምክ ንያቱም በዚህ ላይ እናም ደግሞ ይህን ባቋ ቋሙት ላይ ለበቀል ከመሬት ይጮሃሉና።

፳፭ እናም እንዲህ ይሆናል ሚስጢ ራዊውን ህብረት የመሰረተ የምድርን፣ የሀገሪቷን እና የህዝቡን ᐸነፃነት ለመጣል ይፈልጋል፤ እናም የሀሰት አባት በሆነው፣ እንዲሁም የመጀመሪያ ወላጆቻችንን ᐹያታ ለለው፣ አዎን፣ ይኸው ሀሰተኛ በሆነው የሰ ውን ልጅ ከመጀመሪያ ጀምሮ ባሳሳተው፣ ከመጀመሪያ ጀምሮ የሰዎችንም ልብ ነቢ ያትን እንዲገድሉአቸው፣ በድንጋይ እንዲ ወግሩአቸው፣ እናም እንዲጥሏቸው ባጠጠ ረው በሀሰት አባት በዲያብሎስ የተገነባ ስለ ሆነ፣ ይህም የህዝብን ሁሉ ጥፋት ያመጣል።

፳፮ ስለዚህ፣ ክፉ ነገርም ይወገድ ዘንድ፣ እናም ሰይጣንም በሰው ልጆች ልብ ላይ ᐸኃይል የማያገኝበት፣ ነገር ግን ያለማቋ ረጥ መልካም ነገርን ለመስራት ᐹየሚገፋ ፋበት፣ ወደ ሁሉም ፅድቁ ምንጭ መጥ ተው የሚድኑበት ጊዜ ይመጣ ዘንድ እኔ ሞሮኒ እነዚህን ነገሮች እንድፅፍ ታዘዝኩ።

ምዕራፍ ፱

መንግስቱ ከአንዱ ወደ ሌላኛው በዘር፣ በማ ጭበርበር እናም በግድያ ተላለፈ—ኤመር የፅድቅነትን ልጅ ተመለከተ—ብዙ ነቢ ያት ለንሰሃ ጮኹ—ህዝቡም በረሃብና በመርዛማ እባቦች ተሰቃዩ።

፩ እናም እንግዲህ እኔ ሞሮኒ ታሪኬን እቀ ጥላለሁ። ስለዚህ፣ እነሆ፣ እንዲህ ሆነ በአ ኪሽ እናም በወዳጆቹ ᐸሚስጥራዊ ሴራዎች ምክንያት፤ እነሆ፣ የኦመርን መንግስት ገለ በጡት።

፪ ይሁን እንጂ፤ ጌታ የኦመርንና የእርሱን ጥፋት ለማይፈልጉት፣ ለወንዶችና ለሴቶች ልጆቹ መሃሪ ነበር።

፫ እና ጌታ ኦመር ምድሪቷን ለቆ እን ዲወጣ በህልሙ አስጠነቀቀው፤ ስለሆነም ኦመር ከቤተሰቦቹ ጋር ምድሪቱን ለቆ ወጣ፤ እናም ለብዙ ቀናትም ተጓዘ፣ እናም ወደ ᐸሺም ኮረብታ መጥቶ ኔፋውያን በጠፉ በት ᐹቦታ ደረሱ፣ እናም ከዚያም ወደምስ

፳፩ ᐸ ሔለ. ፮፡ ፳፰።
፳፪ ᐸ ሞር. ፰፡ ፳፯፡ ፵–፵፩።
ᐹ ቅ.መ.መ. በቀል።
፳፫ ᐸ ፩ ኔፊ ፳፪፡ ፳፪–፳፫፤ ሙሴ ፮፡ ፲፭።
፳፭ ᐸ ቅ.መ.መ. ነጻ፣ ነጻነት።
ᐹ ዘፍጥ. ፫፡ ፩–፲፫፤ ፪ ኔፊ ፱፡ ፱፤ ሞዛያ ፲፮፡ ፫፤ ሙሴ ፱፡ ፭–፲፱።
፳፮ ᐸ ፩ ኔፊ ፳፪፡ ፳፮።
ᐹ ፪ ኔፊ ፵፫፡ ፱፤ ሞሮኒ ፯፡ ፲፫–፲፯።
፱ ᐸ ፩ ኔፊ ፳፡ ፱፤ ሞዛያ ፲፮፡ ፫፤ ሙሴ ፱፡ ፭–፲፱።
ᐹ ሞር. ፩፡ ፫፤ ፱፡ ፳፫።
ᐹ ሞር. ፮፡ ፩–፲፭።

ራቅ ሄደ፤ እናም በባህሩ ዳርቻም አብ ሎም ተብሎ በሚጠራው ቦታ ደረሰ እናም በዚያ ስፍራ ድንኳኑን ተከለ፣ ደግሞ ከያሬ ድና ከቤተሰቦቹ በስተቀር ወንዶችና ሴቶች ልጆቹ እናም ሁሉም ቤተሰቦቹ ድንኳኖቻ ቸውን ተከሉ።

፱ እናም እንዲህ ሆነ ያሬድም በክፋት እጅ በህዝቡ ላይ ንጉስ ሆኖ ተቀባ፤ እናም ለአ ኪሽም ሴት ልጁን ለሚስትነት ሰጠው።

፲ እናም እንዲህ ሆነ አኪሽም አማቱን ለመግደል ፈለገ፤ እናም በጥንት ጊዜ በማ ሉት መሃላም እነርሱን እርዳታ ጠየቃቸው፣ እናም አማቱ በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ህዝ ቡን እየተነጋገረ እያለ ገድለውት ለእርሱም ራሱን ሰጡት።

፲፩ ሚስጢራዊው እናም የኃጢአተኞቹ ሕብረት እጅግ በዝቶ ስለነበር፣ የሁሉንም ሕዝብ ልብ አበላሽቶ ነበር፤ ስለዚህ ያሬድ በዙፋኑ ላይ ተገደለ፣ እናም አኪሽ በእርሱ ቦታ ነገሰ።

፲፪ እናም እንዲህ ሆነ አኪሽም በወንድ ልጁ መቅናት ጀመረ፤ ስለዚህ በወህኒ ቤትም ዘጋው፣ እናም እስከሚሞትም ድረስ ትንሽ ምግብ በመስጠት አቆየው።

፲፫ እናም እንግዲህ እንዲሞት የተሰቃየው ልጅ ወንድም (ስሙም ኒምራህ ነበር) አባቱ በወንድሙ ላይ ባደረገው ነገር ተቆጣ።

፲፬ እናም እንዲህ ሆነ ኒምራህ ጥቂት ቁጥር ያላቸውን ሰዎች በአንድነት ሰበሰበ፣ እናም ከምድሪቱ ሸሸ፣ እናም ሄደና ከኦመር ጋር ኖረ።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ አኪሽም ሌሎች ወን ዶች ልጆችን ወለደ፤ እናም በህዝቡም እም ነትን አገኙ፤ ይሁን እንጂ እርሱ እንደፈ ለገው ሁሉንም አይነት ክፋት ለማድረግ ምለውለታል።

፲፮ አሁን አኪሽ ሥልጣን እንደሚፈልግ ሁሉ፣ የአኪሽ ህዝብም ጥቅም ለማግኘት ይፈልጉ ነበር፤ ስለዚህ፣ የአኪሽ ወንዶች ልጆች በገንዘባቸው ብዙ ሰዎች እንዲከተ ሉአቸው ሳቡአቸው።

፲፯ እናም ለብዙ ዓመታት የቆየ ጦርነትም በአኪሽ ወንድ ልጆች እና በአኪሽ መካከል ተጀመረ፤ አዎን፣ በዚያን መንግስት ስር የነበሩት ሰዎች፤ አዎን ከሰላሳዎቹ ሰዎች እናም ከኦመር ቤት ጋር ከሸሹት ሰዎች በስ ተቀር ሁሉም ጠፉ።

፲፰ ስለዚህ፣ ኦመር በድጋሚ ወደ ርስት ምድሩ ተመለሰ።

፲፱ እናም እንዲህ ሆነ ኦመርም አረጀ፤ ይሁን እንጂ፣ በእርጅናው ወቅት ኤመርን ወለደ፤ እናም በእርሱም ምትክ እንዲነግስ ንጉስ እንዲሆን ኤመርን ቀባው።

፲፳ እናም ኤመር ንጉስ እንዲሆን ከቀ ባው በኋላ ለሁለት ዓመታት ያህል በምድ ሪቱ ላይ ሠላምን አገኘ፤ እናም በሀዘን የተ ሞሉ እጅግ ብዙ የሆኖ ቀናትን እየተመለ ከተ ከኖረ በኋላ ሞተ። እናም እንዲህ ሆነ ኤመርም በእርሱ ቦታ ነገሰ እናም የአባቱ ንም አርአያ ተከተለ።

፲፳፩ እናም ጌታ እርግማኑን ከምድሪቱ በድጋሚ ማስወገድ ጀመረ፣ እናም በኤ መር አገዛዝም የኤመር ቤት እጅግ በልፅጎ ነበር፤ እናም ለስልሳ ሁለት ዓመታትም እጅግ ሀብታም እስከሚሆኑ ድረስ እጅግ ጠንካሮች ሆነው ነበር፤

፲፳፪ ከሁሉም ዓይነት ፍራፍሬ፣ እናም እህል፣ እናም ሃር፣ እናም መልካም ናይ ለን፣ እናም ወርቅ፣ እናም ብር፣ እናም የከ በሩ ነገሮች ነበሯቸው፤

፲፳፫ እናም ደግሞ ሁሉም ዓይነት የቀ ንድ ከብት፣ በሬዎች እናም ላሞች፣ እናም በግ፣ እናም አሳማ፣ እናም ፍየሎች፣ እናም ደግሞ ለሰዎች ለምግብነት ጠቃሚ የሆኑ በርካታ ሌሎች እንሰሳት ነበሯቸው።

፲፳፬ እናም ደግሞ ᐸፈረሶች፣ እናም አህ ዮች፣ እናም ዝሆኖች፣ እናም ኩረሎም፣ እናም ኮሞም፣ ነበሩአቸው፤ ሁሉም እናም በተለይ ዝሆኖቹ፣ እናም ኩረሎሞቹም እን ዲሁም ኩሞሞቹ ለሰዎች ጠቃሚ ነበሩ።

፲፳ እናም ጌታም በዚህች ከምድር ሁሉ በላይ ᐸበተመረጠችው መሬት ላይ በረከ

ቱን እንደዚህ አፍስሶአል፤ እናም እርሱም ይህችን ምድር የያዘ ለጌታ እንደሚይዝ አለ በለዚያ ግን በክፋት በደረሱ ጊዜ ግን ፡እን ደሚጠፉ አዟቸዋል፤ እንደዚህ አይነቶቹም ላይ፣ አለ ጌታ፡ የቁጣዬን ሙላት አፈስሳ ለሁና።

፳፩ እናም ኤመር በዘመኑ ሁሉ በፅድቅ ፍርድን ፈፅሟል፤ እናም ብዙ ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወለደ፤ እናም ቆሪያንቱ ምን ወለደ፣ እናም በእርሱ ቦታም እንዲ ነግስ ቀባው።

፳፪ እናም ቆሪያንቱም በእርሱ ምትክ እንዲነግስ ከቀባው በኋላ፣ ለአራት ዓመት ኖረ፣ እናም በምድሪቱም ላይ ሠላምን ተመለከተ፤ አዎን፣ እናም ደግሞም ፡የጻ ድቅነትን ልጅ ተመልክቷል፣ እናም በዘ መኑም ተደስቷል፣ እናም ከብሯል፣ እናም በሰላም ሞተ።

፳፫ እናም እንዲህ ሆነ ቆሪያንቱም የአባ ቱን ዱካ ተከተለ፤ እናም ብዙ ታላላቅ ከተ ሞችን መሰረተ፣ እናም በዘመኑ ሁሉ ለህ ዝቡ መልካም የነበረውን አበረከተ። እናም እንዲህ ሆነ በጣም እስከሚያረጅም ድረስ ልጆች አልነበሩትም።

፳፬ እናም እንዲህ ሆነ ሚስቱም መቶ ሁለት ዓመት ሲሆናት ሞተች። እናም እን ዲህ ሆነ ቆሪያንቱም በእርጅናው ወጣት አገ ልጋይ የሆነችን አገባ፣ እናም ወንዶች እና ሴቶች ልጆችን ወለደ፤ ስለዚህ አንድ መቶ አርባ ሁለት ዓመት እስከሚሆነው ድረስ ኖረ።

፳፭ እናም እንዲህ ሆነ ቆምን ወለደ፣ እናም ቆምም በእርሱ ምትክ ነገሰ፤ እናም እርሱም ለዓርባ ዘጠኝ ዓመታት ነገሰ፤ እናም እርሱም ሔትን ወለደ፤ እናም ደግሞ ሌሎች ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወለደ።

፳፮ እናም ህዝቡም በምድሪቱ ሁሉ ላይ እንደገና ተሰራጨ፣ እናም በድጋሚ በም ድሪቱ ላይ እጅግ ታላቅ የሆነ ኃጢያት ተጀመረ፤ እናም ሔትም አባቱን ለማጥ ፋት የጥንቱን ሚስጥራዊ ዕቅድ በድጋሚ ማቀፍ ጀመረ።

፳፯ እናም እንዲህ ሆነ እርሱም አባቱን በራሱ ጎራዴ በመግደል ከዙፋኑ ላይ አወረ ደው፤ እናም እርሱ በምትኩ ነገሰ።

፳፰ እናም እነርሱም የጌታን መንገድ ማዘ ጋጀት እንዳለባቸው፣ አለበለዚያ በምድሪቱ ላይ እርግማን እንደሚመጣ፣ አዎን ንሰሃ ካልገቡ ታላቅ ረሃብ እንደሚሆን በዚህም ብዙዎች እንደሚጠፉ የሚናገሩ፣ ለንሰሃ የሚጮኹ ነቢያት በድጋሚም በምድሪቱ ላይ መጡ።

፳፱ ነገር ግን ህዝቡ የነቢያቱን ቃላት አላ መኑም፤ ነገር ግን እነርሱን አባረሩአቸው፤ እናም ጥቂቶቹን በጉድጓድ ጣሉአቸው፣ እናም እንዲሞቱ ተዉአቸው። እናም እን ዲህ ሆነ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ያደረጉትም በንጉሱ ሔት ትዕዛዝ መሰረት ነበር።

፴ እናም እንዲህ ሆነ በምድሪቱም ላይ ታላቅ ድርቅ ተጀመረ፣ እናም ነዋሪዎቹም በድርቁ የተነሳ እጅግ ፈጣን በሆነ ሁኔታ ማለቅ ጀመሩ፣ በምድሪቱ ገፅ ላይ ምንም ዝናብ አልነበረምና።

፴፩ እናም እንዲህ ሆነ በምድሪቱ ደግሞ መርዛማ እባቦች መጡ፣ እናም ብዙ ሰዎችን ነደፉአቸው። እናም እንዲህ ሆነ ከብቶቻቸ ውም ከመርዛማው እባቦች ፊት በምድሪቱ በስተደቡብ በኩል በኔፋውያን ፡ዛራሔምላ ተብሎ ወደሚጠራው ሸሹ።

፴፪ እናም እንዲህ ሆነ በሚሸሹበት ጊዜም ብዙዎች ሞቱ፤ ይሁን እንጂ፣ ጥቂቶቹም በምድሪቱ በስተደቡብ በኩል የሸሹ ነበሩ።

፴፫ እናም እንዲህ ሆነ ጌታም ፡እባቦቹ በማሳደድ እንዳይከተሉአቸው፣ ነገር ግን ህዝቡ ማለፍ እንዳይችሉ፣ ለማለፍ የሚ ጥሩትም በመርዛማዎቹ እባቦች ምክንያት እንዲወድቁ እንዲያሰናክሏቸው አደረገ።

፴፬ እናም እንዲህ ሆነ ህዝቡም አራዊ ቶች ያለፉበትን መንገድ ተከተሉ፣ እናም ሁሉንም እስኪመገቡ ድረስ የወዳደቁትን

፳ ሀ ኤተር ፪፡ ፳–፲፭። ፳፪ ሀ ፫ ኔፊ ፳፭፡ ፪። ፴፭ ሀ ኦምኒ ፩፡ ፲፫። ፴፫ ሀ ዘኁል. ፳፩፡ ፮–፱።

የከብት ስጋዎች ይመገቡ ነበር። እንግዲህ ህዝቡም መጥፋት እንዳለባቸው በተመ ለከቱ ጊዜ ለጥፋቶቻቸው ᐧንሰሃ መግባት ጀመሩ፣ እናም ወደ ጌታ ጮኹ።

፴፮ እናም እንዲህ ሆነ በጌታም ፊት እራ ሳቸውን በብቃት ᐧዝቅ ሲያደርጉ፣ እር ሱም በምድሪቱ ገፅ ላይ ዝናብ ላከ፤ እናም ህዝቡም በድጋሚ ነፍስ ዘሩ፣ እናም በምድ ሪቱም ዙሪያ ሁሉ እናም በሃገሪቱ በስተሰ ሜን ፍራፍሬ በቀለ። እናም ጌታም ከረሃብ እነርሱን በመጠበቅ ኃይሉን አሳያቸው።

ምዕራፍ ፲

አንዱ ንጉስ ሌላኛውን ተካ—አንዳንዶቹ ንጉሶች ፃድቅ ናቸው፤ ሌሎች ደግሞ ኃጢአተኞች ናቸው—ፅድቅ የበላይ ሲሆን ህዝቡ በጌታ ይባረካሉ እናም ይበለፅጋሉ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ ሼዝ የሔት ዘር የነበ ረው—ሔት በረሃቡ ሞቷል፣ እናም ከሼዝ በስተቀር ቤተሰቡ በሙሉ ሞቷል—ስለ ዚህ፣ ሼዝም የተጎዱትን ሰዎች ማጠናከር ጀመረ።

፪ እናም እንዲህ ሆነ ሼዝም የአባቶቹን አሟሟት አስታወሰ፣ እናም እርሱም ጻድ ቃዊ የሆነ መንግስት መሰረተ፤ ምክንያቱም እርሱ ጌታ ያሬድን እና ወንድሙን ባህሩን ᐧአሻግሮ ሲያመጣቸው ያደረገውን ያስታ ውሳልና፤ እናም እርሱም የጌታን መንገድ ተከተለ፤ እናም እርሱም ወንዶችን እና ሴቶች ልጆችን ወለደ።

፫ እናም ታላቁ ልጁ፣ ሼዝ ተብሎ የሚ ጠራው በእርሱ ላይ ተነሳበት፤ ይሁን እንጂ ሼዝም እጅግ ሀብታም በመሆኑ በሌቦች ተገ ደለ፣ ይህም ለአባቱ ሠላምን በድጋሚ አስ ገኘ።

፬ እናም እንዲህ ሆነ አባቱም በምድሪቱ ላይ ብዙ ከተሞችን አቋቋመ፣ እናም ህዝቡ በድጋሚ በምድሪቱ ላይ ተሰራጨ። እናም ሼዝም እጅግ እስከሚያረጅ ድረስ ኖረ፤ እናም ሪፕላኪሽን ወለደ። እናም እርሱ ሞተ፤ እናም ሪፕላኪሽ በእርሱ ቦታ ነገሰ።

፭ እናም እንዲህ ሆነ ሪፕላኪሽም በጌታ ዐይን የሚሰራው ትክክል አልነበረም፤ ምክ ንያቱም ብዙ ሚስቶች እና ᐧእቁባቶች ነበ ሩትና፣ እናም በሰዎች ትከሻም ለመሸከም የማይቻል አሳረፈ፣ አዎን፣ ሰዎችንም ከባድ ቀረጥ ይቀርጣቸው ነበር፤ እናም በቀረጡም የሚያምሩ የተስፋፉ ህንጻዎች ይገነባ ነበር።

፮ እናም ለራሱም እጅግ የሚያምር ዙፋን ሠራ፤ እናም ብዙ ወህኒ ቤቶችንም ሠራ እናም ቀረጥ የማይከፍሉትንም ሰዎች ወህኒ ቤት አስገባቸው፤ እናም ቀረጥ ለመክፈል የማይችልም እስር ቤት እንዲገባ ይደረ ጋል፤ እናም እርሱም እራሳቸውን እንዲ ደግፉ ያለማቋረጥ እንዲሰሩ አደረጋቸው፤ እናም ለመስራት ፈቃደኛ ያልሆነውንም እንዲሞት አደረገ።

፯ ስለሆነም መልካም የሆኑ ስራውን በሙሉ አገኘ፤ አዎን፣ መልካም የሆነውን ወርቅም በእስር ቤት እንዲጣራ አደረገ፤ እናም የሚያምረውን የእጅ ሥራም በእ ስር ቤት እንዲሠራ አደረገ። እናም እን ዲህ ሆነ በዝሙቱ እናም በእርኩሰቱ ህዝ ቡን አሳዝኖ ነበር።

፰ እናም ለአርባ ሁለት ዓመታት በነገሰ ጊዜ ህዝቡ በአመፅ በእርሱ ላይ ተነስተው በት ነበር፤ እናም በድጋሚም በምድሪቱ ላይ ጦርነት ተጀመረ፤ በዚህም ሪፕላኪሽ ተገ ደለ፣ እናም ዘሮቹ ከምድሪቱ ተባረሩ።

፱ እናም እንዲህ ሆነ ከብዙ ዓመታት በኋላ፣ ሞሪያንተን (የሪፕላኪሽ ዘር የነበረው) ህዝቡ የተቃወማቸውን ወታደሮች በአንድ ነት ሰበሰበ፣ እናም ወደፊት ሔደ እናም ከህ ዝቡም ጋር ተዋጋ፤ እናም እርሱም በብዙ ከተሞች ላይ ሥልጣን አገኘ፤ እናም ጦርነ ቱም እጅግ የሚያሳዝን ነበር፤ እናም ለብዙ ዓመታትም ቆየ፤ እናም እርሱም በምድሪቱ ሁሉ ላይ ሥልጣንን አገኘ፣ እናም በምድ ሪቱ ላይም እራሱን ንጉስ አደረገ።

፴፩ ᐧ አልማ ፴፩፡ ፴፩፤ ት. እና ቃ. ፻፴፡ ፰።
፴፭ ᐧ ት. እና ቃ. ፭፡ ፹፬።
፲ ᐧ ፪ ᐧ ኤተር ፮፡ ፩–፲፪።
፭ ᐧ ያዕቆ. ፫፡ ፭፤ ሞዛያ ፲፯፡ ፪።

፲ እናም እራሱንም ንጉስ ካደረገ በኋላ የህዝቡን ሽክም አቀለለ፣ በዚህም በህዝቡ አመለካከት ተወዳጅነትን አገኘ፣ እናም እነ ርሱም ንጉሳቸው አድርገው ቀቡት።

፲፩ እናም ህዝቡን በፍትህ ገዛ፣ ነገር ግን በርካታ ዝሙትን ስለሚፈፅም ለራሱ ትክ ክል አላደረገም፤ ስለዚህ ከጌታ ፊት ተለየ።

፲፪ እናም እንዲህ ሆነ ሞሪያንተን ብዙ ከተሞችን ሠራ፣ እናም ህዝቡም በእርሱ ንግስናም በህንፃዎች፣ እናም በወርቅ፣ እናም በብር፣ እናም እህል በማብቀል፣ እናም ከብቶችን በማርባት፣ እጅግ ሀብታ ሞች ሆኑ፣ እናም እንደዚህ አይነት ነገሮ ችም እንደቀደሙት ጊዜያት ሆኑላቸው።

፲፫ እናም ሞሪያንተን እጅግ ታላቅ ለሆነ እድሜ ኖረ፣ እና ከዚያም ቂምን ወለደ፤ እናም ቂምም በአባቱ ምትክ ነገሰ፤ እናም ለስምንት ዓመታት ነገሰ፣ እናም አባቱም ሞተ። እንዲህ ሆነ ቂም በፅድቅ አልነገሰም፣ ስለሆነም በጌታ አልተወደደም።

፲፬ እናም ወንድሙም በአመፅ ተነሳበት፣ በዚህም በእስር እንዲሆን አደረገው፤ እናም በዘመኑ ሁሉ በእስር ቤት ተቀመጠ፤ እናም በእስር እያለ ወንዶች እና ሴቶች ልጆችን ወለደ፣ እናም በእርጅናውም ሌዊን ወለደ፤ እናም ሞተ።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ ሌዊ አባቱ ከሞተ በኋላ ለአርባ ሁለት ዓመታት በእስር ቤት አገለገለ። እናም ከምድሪቱ ንጉስ ጋር ተዋጋ፣ እናም በዚህ መንግስቱን ለራሱ አገኘ።

፲፮ እናም መንግስቱንም እራሱ ካገኘው በኋላ በጌታ ዐይን መልካም የሆነውን አደ ረገ፤ እናም ህዝቦቹ በምድሪቱ ላይ በለፀጉ፣ እናም እስከ እርጅናውም በመልካም ሁኔታ ኖረ፤ እናም ሴቶችን እና ወንዶች ልጆችን ወለደ፤ እናም ደግሞ በእርሱ ምትክ ንጉስ አድርጎ የቀባውን ቆሮምን ወለደ።

፲፯ እናም እንዲህ ሆነ ቆሮምም በዘመኑ ሁሉ በጌታ ፊት መልካም የሆነውን ነገርን ሠራ፤ እናም ብዙ ሴቶች እና ወንዶች ልጆ ችን ወለደ፤ እናም ለረጅም ጊዜ በምድር ላይ ከኖረ በኋላ፣ ልክ እንደሌሎቹ ምድራ ዊያን ሁሉ ህይወቱ አለፈች፤ እናም ኪሽም በእርሱ ምትክ ነገሰ።

፲፰ እናም እንዲህ ሆነ ኪሽም ደግሞ ሞተ፣ እናም ሊብ በእርሱ ምትክ ነገሰ።

፲፱ እናም እንዲህ ሆነ ሊብም ደግሞ በጌታ ፊት መልካም የሆነን ነገር አደረገ። እናም በሊብ ዘመን ᵘመርዛማዎቹም እባቦች ጠፍ ተው ነበር። ስለሆነም ህዝቡም በምድሪቱ በስተደቡብ በኩል ምግብ ለማደን ተጓዙ፣ ምክንያቱም በጫካ አውሬዎች ተሸፍኖ ነበ ርና። እናም ሊብም ደግሞ ታላቅ አዳኝ ሆነ።

፳ እናም በምድሪቱ ቀጭን በሆነው፣ ምድሪቱን የሚከፍለው ባህር ባለበት ᵛፍራ አጠገብ ታላቅ ከተማን ሠሩ።

፳፩ እናም በምድሪቱም በስተደቡብ በኩል ያለውን ምድረበዳ የዱር አውሬ ለማግኘት ሲሉ ጠበቁት። እናም በስተ ሰሜን ያለው ምድር በሙሉ በነዋሪዎች ተሸፍኗል።

፳፪ እናም እነርሱም እጅግ ሠራተኞች ነበሩ፤ እናም እርስ በርሳቸውም ጥቅምን ያገኙ ዘንድ ይጓዙ፣ እናም ይሸጡ፣ እናም ይለዋወጡ ነበር።

፳፫ እናም በሁሉም አይነት የብረት አፈር፣ እናም ወርቅ፣ እናም ብር፣ እናም ᵘብረት፣ እናም ነሀስ፣ እናም ሁሉም አይ ነት ብረታ ብረቶች ይሰሩ ነበር፤ እናም ከመሬትም ቆፍረው ያወጡት ነበር፤ ስለ ዚህ፣ ከወርቅ፣ እናም ከብር፣ እናም ከብ ረት፣ እናም ከመዳብ የብረት አፈር ለማ ግኘት አፈር ይቆልሉ ነበር። እናም መል ካም ሥራዎችን ሁሉ ሠርተዋል።

፳፬ እናም ሀርና የተፈተለ ጥሩ በፍታ ነበራቸው፤ እናም ዕርቃናቸውን ይሸፍኑበ ትም ዘንድ ሁሉንም አይነት ልብሶች ሠሩ።

፳፭ እናም መሬቱን ለማረስ፣ እናም አር ሰውም ለመዝራት፤ ለመሰብሰብ፣ እናም ለመቆፈር፣ እናም ደግሞ ለመውቃት ሁሉ ንም አይነት መሳሪያዎች ሠሩ።

ᵘ፲፱ ሆ ኤተር ፱፡፴፭። ᵛ፳፫ ሆ ፪ ኔፊ ፭፡፲፭።

፳፯ እናም በእንሰሳቶቹም ተረድተው ስራቸውን ለመስራት ሁሉንም መሳሪያ ዎች ሠሩ።

፳፰ እናም ሁሉንም አይነት የጦር መሳሪ ያዎች ሠሩ። እናም እጅግ አስገራሚ የእጅ ሥራዎችን ሁሉ ሠሩ።

፳፱ እናም ማንኛውም ህዝብ ከዚህ የበ ለጠ ሊባረክ እናም በጌታም እጅ በጭራሽ ሊሳካለት አይቻለውም። እናም ከምድሪ ቱም ይበልጥ በተመረጠችው ምድር ላይ ነበሩም፣ ጌታ ይህን ተናግሯልና።

፴፬ እናም እንዲህ ሆነ ሊብ ለብዙ ዓመ ታት ኖረ፣ እናም ወንዶችና ሴቶች ልጆ ችን ወለደ፤ እናም ደግሞ እርሱም ሔርቶ ምን ወለደ።

፴፩ እናም እንዲህ ሆነ ሔርቶምም በአባቱ ምትክ ነገሰ። እናም ሔርቶም ለሃያ አራት ዓመታት በነገሰ ጊዜ፣ እነሆ፣ መንግስቱ ከእርሱ ተወሰደ። እናም ለብዙ ዓመታት፣ አዎን በቀሪው ዘመኑ ሁሉ በግዞት አገለገለ።

፴፪ እናም ሔትን ወለደ፣ እናም ሔትም በዘመኑ ሁሉ በግዞት ኖረ። እናም ሔትም አሮንን ወለደ፣ እናም አሮንም በዘመኑ ሁሉ በእስር ኖረ፤ እናም እርሱም አምኒጋ ዳን ወለደ፣ እናም አምኒጋዳም ደግሞ በዘ መኑ ሁሉ በግዞት ኖረ፤ እናም እርሱም ቆሪያንቱምን ወለደ፣ እናም ቆሪያንቱምም በዘመኑ ሁሉ በግዞት ኖረ፤ እናም እርሱም ቆምን ወለደ።

፴፫ እናም እንዲህ ሆነ ቆምም ከመንግ ስቱ ግማሽ የሚሆነውን ወደ እርሱ ሳበ። እናም እርሱም በግማሽ መንግስቱ ለአርባ ሁለት ዓመታት ነገሠ፤ እናም እርሱም ከን ጉስ አምጊድ ጋር ለመዋጋት ሔደ፤ እናም እነርሱም ለብዙ ዓመታት ተዋጉ፣ በዚያን ጊዜም ቆም በአምጊድ ላይ ኃይልን አገኘ እናም በተቀረው መንግስት ላይም ኃይልን አገኘ።

፴፫ እናም በቆም ዘመንም በምድሪቱ ዘራፊዎች መምጣት ጀመሩ፤ እናም የጥን ቱን ዕቅድ ተከተሉ፤ እናም እንደጥንቱም [ሀ]መሃላቸውን ፈፀሙ፣ እናም መንግስቱን ለማጥፋት በድጋሚ ተመኙ።

፴፬ እንግዲህ ቆምም ከእነርሱ ጋር ለረ ጅም ጊዜ ተዋጋ፤ ይሁን እንጂ፣ አላሸነ ፋቸውም ነበር።

ምዕራፍ ፲፭

የያሬዳውያን ህይወት በጦርነት፤ በፀብ እና በክፋት የተሞላ ነበር—ያሬዳውያን ንሰሃ ካልገቡ ፈፅመው እንደሚጠፉ ነቢያት ተንብየዋል—ህዝቡም የነቢያትን ቃላት አልተቀበሉም።

፩ እናም ደግሞ በቆም ዘመን ብዙ ነቢያት ተነሱ፣ እናም ያ ታላቅ ህዝብም ንሰሃ ካልገባ እናም ወደጌታ ካልተመለሱ፣ እናም ግድ ያቸውን እናም ክፋታቸውን ካላቆሙ እን ደሚጠፉ ትንቢት ተናገሩ።

፪ እናም እንዲህ ሆነ ነቢያቱም በህ ዝቡ ተቀባይነትን አላገኙም ነበር፣ እናም ህዝቡም ሊገድሏቸው ስለፈለጉ የቆምን ጥበቃ ለማግኘት ወደ እርሱ ሸሹ።

፫ እናም ለቆምም ብዙ ነገሮችን ተነበዩ ለት፤ እናም እርሱም በቀሪው ዘመኑ ሁሉ የተባረከ ነበር።

፬ እናም በመልካም እርጅና ሁኔታ ውስጥ ኖረ፣ እናም ሺብሎምንም ወለደ፤ ሺብሎ ምም በእርሱ ምትክ ነገሰ። እናም የሺብሎ ምም ወንድም በእርሱ ላይ አመፀበት፣ እናም በምድሪቱ ሁሉ እጅግ ታላቅ የሆነ ጦርነትም ተጀመረ።

፭ እናም እንዲህ ሆነ የሺብሎም ወንድ ምም ስለህዝቡ መጥፋት የተነበዩት ነቢያት በሙሉ እንዲገደሉ አደረገ፤

፮ እናም በምድሪቱ ሁሉ ታላቅ መቅሰ ፍት ሆነ፣ ምክንያቱም ለኃጢአታቸውም ንሰሃ ካልገቡ ታላቅ እርግማን በምድሪቱ ላይ፣ እናም ደግሞ በህዝቡ ላይ እንደ ሚሆን፣ እናም ከዚህ በፊት በምድር ላይ ታይቶ የማይታወቅ ታላቅ ጥፋትም በመካ ከላቸው እንደሚሆን፣ እናም ንሰሃ ካልገቡ

[ሀ] መሃላ፤ የሚስጥር ስብሰባ።

አጥንቶቻቸውም በመሬት ላይ እንደተራራ
ʺእንደሚቆለሉም መስክረዋልና።
፯ እናም በክፉው ህብረታቸው የተነሳ የጌ
ታን ድምፅ አላዳመጡም፤ ስለዚህ፣ በም
ድሪቱ ሁሉ ጦርነት እናም ፀብ ተጀመረ፣
እናም ደግሞ ብዙ ረሃብ እና ቸነፈር ሆነ፤
በዚህም የተነሳ ታላቅ ጥፋት ከዚህ በፊት
በምድር ላይ ታይቶ የማይታወቅ ሆነ፤ እናም
ይህ ሁሉ የሆነው በሺብሎም ዘመን ነበር።
፰ እናም ህዝቡም ለጥፋቶቻቸው ንስሃ
መግባት ጀመሩ፤ እናም ይህንንም ባደረጉ
ጊዜ ጌታ በእነርሱ ላይ ʺምህረት አደረገ
ላቸው።
፱ እናም እንዲህ ሆነ ሺብሎም ተገደለ፤
እናም ሴትም ወደ ምርኮ ተወሰደ፣ እናም
በዘመኑ ሁሉ በምርኮ ኖረ።
፲ እናም እንዲህ ሆነ ልጁ አሃህ መንግስቱን
አገኘ፤ እናም በዘመኑ ሁሉ በህዝቡ ላይ ነገሰ።
እናም እርሱም በዘመኑ ብዙ አይነት ክፋቶ
ችን አደረገ፤ በዚያም ብዙ ደም እንዲፈስ
አደረገ፤ እናም የእርሱም ዘመን ጥቂት ነበር።
፲፩ እናም ኤተም፣ የአሃህ ወገን በመሆኑም
መንግስቱን አገኘ፤ እናም እርሱም ደግሞ
በዘመኑ መጥፎ የሆነውን አደረገ።
፲፪ እናም እንዲህ ሆነ በኤተም ዘመን ብዙ
ነቢያቶች መጡ፣ እናም በህዝቡም ላይ ትን
ቢትን ተናገሩ፤ አዎን፣ ለኃጢአቶቻቸው
ንስሃ ካልገቡ በስተቀር ጌታ ፈፅሞ ከምድር
ላይ እንደሚያጠፋቸውም ተነበዩ።
፲፫ እናም እንዲህ ሆነ ህዝቡም ልባቸውን
አጠጠሩ፤ እናም ቃላቸውንም ʺአላዳመ
ጡም፤ እናም ነቢያቶቹም አዘኑ እናም ከህ
ዝቡ መካከል ወጡ።
፲፬ እናም እንዲህ ሆነ ኤተም በዘመኑ
ሁሉ በክፋት ፍርድን ፈፀመ፤ እናም ሞሮ
ንን ወለደ። እናም እንዲህ ሆነ ሞሮንም
በእርሱ ምትክ ነገሰ፤ ሞሮንም በጌታ ፊት
መጥፎ የሆነውን አደረገ።
፲፭ እናም እንዲህ ሆነ ስልጣንን እናም
ጥቅምን ለማግኘት በተቋቋመው ሚስጢ
ራዊ ሴራ የተነሳ በህዝቡ መካከል ʺአመፅ
ተነሳ፤ እናም በእነርሱም መካከል በክ
ፋት ኃያል የሆነ ሰው ተነሳ፣ እናም እር
ሱም ከሞሮን ጋር ተዋጋ፣ ከዚያም የመንግ
ስቱን ግማሽ አሸነፈ፤ እናም እርሱም ለብዙ
ዓመታት ግማሹን መንግስት አስተዳደረ።
፲፮ እናም እንዲህ ሆነ ሞሮንም አሸነፈው፣
እናም መንግስቱን በድጋሚ ያዘ።
፲፯ እናም እንዲህ ሆነ ሌላም ኃያል ሰው
ተነሳ፤ እርሱም የያሬድ ወንድም ወገን
ነበር።
፲፰ እናም እንዲህ ሆነ እርሱም ሞሮ
ንን በማሸነፍ መንግስቱን ያዘ፤ ስለሆነም፣
ሞሮን በተቀረው ዘመኑ በግዞት ኖረ፤ እናም
እርሱም ቆሪያንቶር ወለደ።
፲፱ እናም እንዲህ ሆነ ቆሪያንቶር በዘመኑ
ሁሉ በግዞት ኖረ።
፳ እናም በቆሪያንቶርም ዘመን ደግሞ ብዙ
ነቢያቶች ተነሱ፣ እናም ታላቅ እናም አስገ
ራሚ ነገሮችን ተነበዩ፣ እናም ወደ ህዝቡም
ለንሰሃ ጮኹ፣ እናም ንሰሃ ካልገቡ በስተ
ቀር ጌታ እግዚአብሔርም እነርሱን ፈፅሞ
በማጥፋት ʺፍርዱን እንደሚፈፅም ተናገሩ፤
፳፩ እናም ጌታ እግዚአብሔር በስልጣኑ
አባቶቻቸውን እንዳመጣ ʺሌሎች ሰዎች
ምድሪቱን እንዲወርሱ እንደሚልክ ወይም
እንደሚያመጣ ተናገሩ።
፳፪ እናም እነርሱም በሚስጢራዊው ህብ
ረት እናም ክፉ በሆነው እርኩሰታቸው የነ
ቢያቱን ቃላት በሙሉ አልተቀበሉም።
፳፫ እናም እንዲህ ሆነ ቆሪያንቶር ʺኤተ
ርን ወለደ፣ እናም በዘመኑ ሁሉ በግዞት ኖሮ
ሞተ።

ምዕራፍ ፲፪

*ነቢዩ ኤተር ህዝቡ በእግዚአብሔር እንዲ
ያምኑ አበረታታ—ሞሮኒ አስገራሚ የሆ*

፲፩ ፯ሀ ኦምኒ ፩፥፳፪፤ ኤተር ፲፬፥፳፩።
፰ሀ ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።
፲፫ሀ ሞዛያ ፲፯፥፪።
፲፭ሀ ቅ.መ.መ. አመጽ።
፳ሀ ቅ.መ.መ. ዳኛ፣ ፍርድ።
፳፩ሀ ኤተር ፲፫፥፳–፳፩።
፳፫ሀ ኤተር ፩፥፮፤ ፲፭፥፴፫–፴፬።

ኑትን እናም በእምነት የተሰሩትን ድንቅ ነገሮች አስታወሰ—የያሬድ ወንድም እም ነቱ ክርስቶስን ለማየት አስቻለው—ጌታ ሰዎች ትሁት ይሆኑ ዘንድ ድካምን ይሰጣ ቸዋል—የያሬድ ወንድም የዜሪንን ተራራ በእምነት አንቀሳቀሰ—እምነት፣ ተስፋ፣ እና ልግስና ለደህንነት አስፈላጊ ናቸው—ሞሮኒ ኢየሱስን ፊት ለፊት አየው።

፩ እናም እንዲህ ሆነ የኤተር ዘመን [ሀ]በቆ ሪያንተመር ዘመን ነበር፤ እናም ቆሪያንተ መር በምድሪቱ በሙሉ ላይ ንጉስ ነበር።

፪ እናም [ለ]ኤተርም የጌታ ነቢይ ነበር፤ ስለ ዚህ ኤተር በቆሪያንተመር ዘመን ተነሳ፤ እናም ለህዝቡ መተንበይ ጀመረ፣ በውስጡ በነበረው የጌታ መንፈስ መንስኤ [ሐ]ሊታገት አይቻልምና።

፫ እርሱም ከማለዳ ጀምሮ ፀሐይ እስከ ምትጠልቅ ህዝቡም ንሰሃ በመግባት በእ ግዚአብሔር እንዲያምኑ አለበለዚያ [መ]እን ደሚጠፉ በመምከር፣ ለእነርሱም [ሠ]በእም ነት ሁሉም ነገሮች ለመሟላት እንደሚችሉ በመንገር [ረ]ጮኸ—

፬ ስለሆነም፣ በእግዚአብሔር የሚያምን በእርግጥ ለተሻለ ዓለም፣ አዎን፣ በእግዚአ ብሔር ቀኝ እጅ በኩል ያለውን ስፍራ እንኳ ለማግኘት [ሰ]ተስፋ ይኖረዋል፤ ይኸውም ተስፋ በእምነት የሚመጣ ነው፤ ተስፋም ለሰዎች ነፍስ [ቀ]እንደመሃልቅ ነው፤ እነርሱ ንም ፅኑ እና የማይነቃነቁ እንዲሆኑ እናም ሁልጊዜም በርካታ [በ]መልካም ነገሮችን እን ዲሰሩ፤ እግዚአብሔርንም [ተ]እንዲያከብሩ ያደርጋቸዋል።

፭ እናም እንዲህ ሆነ ኤተር ታላቅ እና አስ ገራሚ ነገሮችን ለህዝቡ ተነበየላቸው፤ እነ ርሱ ግን ስላላዩት አላመኑበትም።

፮ እናም አሁን፣ እኔ ሞሮኒ፣ ስለነዚህ ነገ ሮች በመጠኑ እናገራለሁ፤ [ተ]እምነት [ሀ]ተስፋ የምናደርጋቸው ነገሮች ነገር ግን [ለ]የማናያ ቸው መሆኑን ለዓለምም አሳያለሁ፤ ስለ ዚህ፣ ስላላያችሁ አትከራከሩ፣ ምክንያቱም እምነታችሁ [ሐ]እስከሚፈተን ድረስ ምስክ ርነትን አትቀበሉምና።

፯ ምክንያቱም ክርስቶስ ከሞት ከተነሳ በኋላ እራሱን ለአባቶቻችን ያሳየው በእም ነት ነበር፤ እነርሱም በእርሱ እምነት እስ ከሚኖራቸው ድረስ እራሱን አልገለፀላቸ ውም፤ ስለሆነም፣ አንዳንዶቹ በእርሱ ላይ እምነት ሳይኖራቸው አልቀረም፣ ምክንያ ቱም እራሱን ለዓለም አላሳየምና።

፰ ነገር ግን ሰዎች በማመናቸው እራሱን ለዓለም አሳይቷል፣ እናም የአብንም ስም አክብሯል፣ እና ሌሎች ከሰማያዊው ስጦታ ይካፈሉ ዘንድ፣ ባልተመለከቷቸውም ነገ ሮች ተስፋ ያደርጉ ዘንድ መንገዱን አዘ ጋጅቷል።

፱ ስለዚህ፣ እናንተ ደግሞ ተስፋን ማድ ረግ፣ እናም እምነት ካላችሁ ከስጦታው ተካፋዮች ለመሆን ትችላላችሁ።

፲ እነሆ የጥንቶቹም ቅዱስ ወደሆነው የእ ግዚአብሔር ስርዓት [ሀ]የሚጠሩት በእምነታ ቸው ነበር።

፲፩ ስለሆነም፣ በእምነት ነበር የሙሴ ህግ የተሰጠው። ነገር ግን እግዚአብሔርም በልጁ ስጦታም ይበልጥ [ለ]የተመረጠውን መንገድ አዘጋጅቷል፤ እናም ይህም የተ ሟላው በእምነት ነው።

፲፪ በሰው ልጆች መካከል [ሀ]እምነት ከሌለ

፲፪ ፩ *ሀ* ኤተር ፲፫፡ ፲፫–፴፩።
፪ *ሀ* ቅ.መ.መ. ኤተር።
ለ ኤር. ፳፡ ፱፤ ኢኖስ ፩፡ ፳፯፤ አልማ ፶፫፡ ፩።
፫ *ሀ* ኤተር ፲፩፡ ፲፪፣ ፳–፳፪።
ለ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
ሐ ት. እና ቃ. ፲፲፪፡ ፭።
፬ *ሀ* ቅ.መ.መ. ተስፋ።
ለ ዕብ. ፮፡ ፲፱።
ሐ ፩ ቆሮ. ፲፭፡ ፶፭።
መ ፫ ኔፊ ፲፪፡ ፲፯።
ሠ *ሀ* ዕብ. ፲፩፡ ፩።
ረ ሮሜ ፰፡ ፳፬–፳፭።
ሰ አልማ ፴፪፡ ፳፩።
ቀ ፫ ኔፊ ፳፯፤ ፲፩፣ ት. እና ቃ. ፲፭፡ ፲፱፣ ፲፲፣ ፲፳፩፡ ፯–፰።
በ ዕብ. ፲፫፡ ፲፮።
ተ ፩ ቆሮ. ፲፫፡ ፲፫።
ቸ *ሀ* ዕብ. ፲፩፡ ፩።
ኀ *ሀ* ቅ.መ.መ. ኤተር።
ነ *ሀ* ኤር. ፳፡ ፱፤ ኢኖስ ፩፡ ፳፯፤ አልማ ፶፫፡ ፩።
፲ *ሀ* ኤተር ፲፩፡ ፲፪፣ ፳–፳፪።
ለ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
ሐ ት. እና ቃ. ፲፲፪፡ ፭።
፲፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. ተስፋ።
ለ ኤፍ. ፳፡ ፱፤ ኢኖስ ፩፡ ፳፯፤ አልማ ፶፫፡ ፩።
፲፪ *ሀ* ኤተር ፲፫፡ ፲፫–፴፩።
ለ ቅ.መ.መ. ኤተር።
ሐ ኤር. ፳፡ ፱፤ ኢኖስ ፩፡ ፳፯፤ አልማ ፶፫፡ ፩።
መ ፫ ኔፊ ፲፪፡ ፲፯።
ሠ ፩ ቆሮ. ፲፫፡ ፲፫።
ረ ሮሜ ፰፡ ፳፬–፳፭።
ሰ ፩ ቆሮ. ፲፫፡ ፲፫።
ቀ ፫ ኔፊ ፳፯፤ ፲፩፣ ት. እና ቃ. ፲፲፪፡ ፭–፲፩።
በ ዕብ. ፲፩፡ ፩–፲፫።
ተ ፩ ቆሮ. ፲፫፡ ፲፫–፲፮።
ቸ ፩ ቆሮ. ፲፫፡ ፲፫–፲፮።
ኀ ፩ ቆሮ. ፲፫፡ ፲፫–፲፮።
ነ *ሀ* ኤተር ፲፫፡ ፲፫–፴፩።
ለ ቅ.መ.መ. ኤተር፣ በእግዚአብሔር መጠራት፣ የተጠራበት።
ሐ *ሀ* ፩ ቆሮ. ፲፪፡ ፴፩።
መ *ሀ* ፪ ኔፊ ፳፯፤ ፳ሀ፡ ሞዛያ ፳፡ ፲፳፣ ሞሮኒ ፯፡ ፴፯፣ ት. እና ቃ. ፴፭፡ ፳–፲፩።

እግዚአብሔር በመካከላቸው ^ተአምር መስራት አይችልም፤ ስለሆነም እስከሚ ያምኑ ድረስ እራሱን አልገለፀላቸውም።

፲፫ እነሆ፣ የአልማ እና የአሙሌቅ እምነ ትም ነው *ወህኒ ቤቱ ወደምድር እንዲወ ድቅ ያደረገው።

፲፬ እነሆ፣ የኔፊና የሌሂ እምነት ነበር ላማናውያንን *እንዲለወጡ ያደረገው፣ ስለሆነም እነርሱም በእሳት እና ^በመንፈስ ቅዱስ ተጠመቁ።

፲፭ እነሆ፣ *የአሞን እና የወንድሙ እም ነት ነበር ታላቅ የሆነ ተአምር በላማናውያን መካከል ^የሠራው።

፲፮ አዎን፣ ከክርስቶስ በፊት የነበሩትም እንኳን እናም ደግሞ ከእርሱ በኋላ የነበ ሩት *ተአምር የሚሰሩት ሁሉም የሰሯቸው ^በእምነት ነበር።

፲፯ እናም ሦስቱ ደቀመዛሙርት ሞትን *እንዳይቀምሱ ቃል ኪዳን የተገባላቸው በእምነት ነበር፤ እናም እምነት እስከሚኖ ራቸው ድረስ ቃልኪዳኑን አላገኙም ነበር።

፲፰ እናም በማንኛውም ጊዜም እንኳን እምነት እስከሚኖራቸው ድረስ ተአምራ ትን ማንም አልሰራም፤ ስለዚህ እነርሱ አስ ቀድመው በእግዚአብሔር ልጅ አምነዋል።

፲፱ እናም ክርስቶስ *ከመምጣቱም በፊት እንኳን በእምነታቸው እጅግ የበረቱ ብዙ ዎች ነበሩ፤ እነርሱም ^በመጋረጃው ስር ሊጠበቁ አልተቻሉም፤ ነገር ግን በእው ነትም በእምነት አይን ያዩአቸውን ነገሮች በዐይኖቻቸው አይተዋል እናም ተደስተ ዋል።

፳ እናም እነሆ፣ በዚህ መዝገብ ውስጥም ከእነዚህ አንዱ የያሬድን ወንድም መሆኑን አይተናል፤ እርሱም በእግዚአብሔር እም ነቱ ታላቅ በመሆኑ እግዚአብሔርም *በጣ ቶቹ ሲያመለክት፣ ለእርሱም በተናገራቸው ቃላት ምክንያት፣ ከያሬድ ወንድም እይታ ሊደብቀው አልቻለም፤ ቃላቱንም እርሱ በእምነቱ ያገኛቸው ነበሩ።

፳፩ እናም የያሬድ ወንድም የጌታን ጣት ከተመለከተ በኋላ፣ የያሬድ ወንድም በእ ምነቱ *ቃል ኪዳን ስለተቀበለ፣ ጌታ ከእርሱ ምንም ነገር ከእይታው ሊሰውርበትም አል ቻለም፤ ስለዚህ እርሱም ሁሉንም ነገሮች አሳየው ምክንያቱም ^ከመጋረጃው ውጪ ከእንግዲህ ሊያስቀምጠው አይቻለውምና።

፳፪ እናም እነዚህ ነገሮች በአህዛብ አማ ካኝነት ለወንድሞቻቸው እንዲመጡ አባ ቶቻችን *ቃል ኪዳንን ያገኙት በእምነት ነው፤ ስለዚህ ጌታ፣ አዎን ኢየሱስ ክርስ ቶስም እንኳን፣ እኔን አዘኛል።

፳፫ እናም እንዲህ ስል ተናገርኩት፡ ጌታ ሆይ፣ ስንፅፍ *ደካሞች በመሆናችን አህዛብ ይሳለቁብናል፤ ጌታ በእምነታችን በሚገባ እንድንናገር አድርጎናል፣ ነገር ግን በጽሁፍ ^ኃያላን እንድንሆን አላደረገንምና፤ መን ፈስ ቅዱስንም ስለሰጠሃቸው እነዚህን ሰዎች ሁሉ ብዙ ለመናገር እንዲችሉ አድርገሃ ቸዋልና።

፳፬ እናም በእጆቻችን አስቸጋሪነት ምክ ንያትም ትንሽ ብቻ *እንድንፅፍ አድርገሽ ናል። እነሆ፣ እንደያሬድ ወንድም በይበልጥ መፃፍ እንድንችል አላደረግኽንም፣ ምክ ንያቱም ሰዎች እንዲያነቡት የሚገፋፉበት ኃያል እንዲሆኑ እርሱ የፃፋቸውን ነገሮች እንዳንተው ሁሉ ኃያል አድርገሃቸዋል።

፳፭ ቃላቶቻችንን ደግሞ መፃፍ እስከማን

፲፪ *ለ* ማቴ. ፲፫፡፶፰፤ ሞር. ፱፡፳፡ ፲ *ሀ* አልማ ፲፡፳፡፳፯–፳፱። ፲፡ *ሀ* ሔለ. ፭፡፱–፲፪። *ለ* ሔለ. ፭፡፴፭፤ ፮ ኔፊ ፱፡፳፡ ፲፩ *ሀ* አልማ ፲፯፡፳፱–፴፱። *ለ* ይህም በአለማ ፲፯–፳፯ ውስጥ እንደተነገረው ማለት ነው። ፲፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. ተአምራት። *ለ* ዕብ. ፲፩፡፯–፣ ፲፱ *ሀ* ፮ ኔፊ ፳፡፳፡፯፤ ሞር. ፰፡፲–፲፪። ፲፱ *ሀ* ፪ ኔፊ ፲፩፡፩–፱፤ ያዕቆ. ፱፡፱–፭፤ ጄረም ፩፡፲፩፤ አልማ ፳፭፡፲፫–፲፯። *ለ* ኤተር ፮፡፯። ቅ.መ.መ. ዐይነ-እርግብ። ፳ *ሀ* ኤተር ፮፡፱። ፳፩ *ሀ* ኤተር ፮፡፳፭–፳፯። *ለ* ኤተር ፮፡፳፡ ት. እና ቃ. ፳፯፡፲–፲፮። ፳፪ *ሀ* ኢኖስ ፩፡፲፮። ፳፮ *ሀ* ሞር. ፰፡፲፯፤ ፱፡ ፴፮። *ለ* ፪ ኔፊ ፴፮፡፩። ፳፬ *ሀ* ቅ.መ.መ. ቋንቋ።

ችል ድረስ ኃያል እና ታላቅ አደረክ፤ ስለዚህ
በምንፅፍበት ጊዜም ደካማነታችንን እንመ
ለከታለን፣ እናም ቃላቶቹን በምናስቀምጥ
በትም እንደናቀፋለን፤ እናም አህዛብ በቃ
ላችን [ሀ]እንደሚሳለቁብን እፈራለሁ።
፳፮ እናም ይህን በምናገርበት ጊዜ፣ ጌታ
እንዲህ ሲል ተናገረኝ፥ ሞኞች [ሀ]ይሳለቃሉ
ነገር ግን ያዝናሉ፤ እናም ፀጋዬ ለየዋሆች
በቂ ነው፣ እነርሱም በድካማችሁ ብልጫ
አይወስዱባችሁም።
፳፯ እናም ሰዎች ወደ እኔ የሚመጡ ከሆኑ
[ሀ]ድክመታቸውን አሳያቸዋለሁ። ሰዎች
ትሁት እንዲሆኑ ድካምን [ለ]እሰጣቸዋለሁ፤
እናም [ሐ]ፀጋዬም እራሳቸውን በፊቴ [መ]ዝቅ
ላደረጉ ሁሉ በቂ ነው፤ እነርሱም በፊቴ
እራሳቸውን ዝቅ ካደረጉ፣ እናም በእኔም
እምነት ካላቸው፣ ከዚያም [ሠ]ደካማ የሆኑትን
ለእነርሱ ጠንካራ እንዲሆኑ አደርጋለሁ።
፳፰ እነሆ፣ ለአህዛብ ድካማቸውን አሳያ
ቸዋለሁ፣ እናም [ሀ]እምነት፤ ተስፋ እና ልግ
ስና ወደ እኔ—የፅድቅ ምንጭ ሁሉ ወደ
ሆነው እንደሚያመጣቸው አሳያቸዋለሁ።
፳፱ እናም እኔ ሞሮኒ፣ እነዚህን ቃላት
በመስማቴ ተፅናንቼ ነበር እናም እንዲህ
አልኩኝ፥ አቤቱ ጌታ የፅድቅ ፈቃድህ ይከ
ናወናል፤ ምክንያቱም አንተ ለሰው ልጆች
እንደእምነታቸው እንደምታከናውን አው
ቃለሁና፤
፴ የያሬድ ወንድም የዜሪንን ተራራ ተን
ቀሳቀስ ሲለው—እርሱም [ሀ]ተንቀሳቀሶ
ነበር። እናም እምነት ባይኖረው አይንቀሳ
ቀስም ነበር፣ ስለዚህ አንተም ለሰዎች እንደ
እምነታቸው ትሰራለህ።
፴፩ ምክንያቱም ለደቀመዛሙርቱም ራስ
ህን እንደዚህ አሳይተሃል፤ ባንተም [ሀ]ካመኑ
እናም በስምህ ከተናገሩ በኋላ ራስህን በታ
ላቅ ኃይል አሳይተሃቸዋልና።
፴፪ እናም ደግሞ ለሰዎች ቤት፣ አዎን፣
በአባትህም [ሀ]ቤት እንኳን ማዘጋጀትህን
መናገርህን አስታውሳለሁ፤ በዚህም ሰው
የላቀ [ለ]ተስፋ ይኖረው ዘንድ ነው፤ ስለሆ
ነም ሰው ተስፋ ማድረግ ይገባዋል፣ አለበ
ለዚያ አንተ ያዘጋጀኸውን ሥፍራ በውርስ
ሊቀበል አይችልም።
፴፫ እናም በድጋሚ፣ ለሰዎች ልጆች
ስፍራቸውን ለማዘጋጀት እንደገና ታነሳው
ዘንድ ህይወትህን አሳልፈህ ለአለም እስከ
መስጠት ድረስ ዓለምን [ሀ]መውደድህን መና
ገርህን አስታውሳለሁ።
፴፬ እናም አሁን ይህ ለሰዎች ልጆች የነ
በረህ [ሀ]ፍቅር ልግስና እንደሆነ አውቃለሁ፤
ስለዚህ ሰዎች ልግስና ከሌላቸው በአባትህ
መኖሪያ ያዘጋጀኸውን ስፍራ ሊወርሱ አይ
ችሉም።
፴፭ ስለዚህ፣ እኛ ደካሞች በመሆናችን
አህዛብ ልግስና ከሌላቸው ትፈትናቸዋ
ለህ እናም [ሀ]ተሰጦአቸውም ይወሰድባቸ
ዋል፤ አዎን፣ ያንን የተቀበሉትንም እን
ኳን፣ እናም በብዛት ላላቸውም ይጨመር
ላቸዋል ያልከውን በዚህ ነገር አውቀዋለሁ።
፴፮ እናም እንዲህ ሆነ አህዛብ ልግስና
ይኖራቸው ዘንድ [ሀ]ጸጋ እንዲሰጣቸው ወደ
ጌታ ፀለይሁ።
፴፯ እናም እንዲህ ሆነ ጌታም እንዲህ
አለኝ፥ ልግስና ከሌላቸው አንተ ግድ
የለህም፣ አንተ ታማኝ ነበርክ፤ ስለዚህ፣

፳፭ ሀ ፩ ቆሮ. ፪፥፲፬።
፳፮ ሀ ገላ. ፮፥፯።
፳፯ ሀ ያዕቆ. ፬፥፯።
ለ ዘፀአ. ፬፥፲፩፤
፩ ቆሮ. ፩፥፳፯።
ሐ ቅ.መ.መ. ጸጋ።
መ ሉቃ. ፲፰፥፲–፲፬፤
ት. እና ቃ. ፩፥፳፰።
ቅ.መ.መ. ትሁት፣ ትሕትና።
ሠ ሉቃ. ፱፥፵፮–፵፰፤
፪ ቆሮ. ፲፪፥፱።
፳፰ ሀ ፩ ቆሮ. ፲፫፤
ሞሮኒ ፯፥፴፱–፵፯።
፴ ሀ ማቴ. ፲፯፥፳፤
ያዕቆ. ፬፥፮፤
ሔለ. ፲፥፮፣ ፱።
ቅ.መ.መ. ሀይል።
፴፩ ሀ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
፴፪ ሀ ዮሐ. ፲፬፥፪፤
ኢኖስ ፩፥፳፯፤
ት. እና ቃ. ፸፪፥፬፤
፺፰፥፲፰።
ለ ቅ.መ.መ. ተስፋ።
፴፫ ሀ ዮሐ. ፫፥፲፮–፲፯።
፴፬ ሀ ሞሮኒ ፯፥፵፯።
ቅ.መ.መ. ልግስና፤
ፍቅር።
፴፭ ሀ ማቴ. ፳፭፥፲፬–፴።
ቅ.መ.መ. መክሊት፤
ስጦታ።
፴፮ ሀ ቅ.መ.መ. ጸጋ።

ልብስህ [ሀ]ይነፃል። እናም [ለ]ድካምህን በማየ
ትህ በአባቴ ቤት ባዘጋጀሁልህ ቦታ እንድ
ትቀመጥ ጠንካራ ትደረጋለህ።
፴፰ እናም አሁን እኔ ሞሮኒ፣ አህዛቦችን
አዎን እናም ደግሞ የምወዳቸው ወንድሞ
ቼን በክርስቶስ [ሀ]የፍርድ ወንበር ፊት እስ
ካገኛቸው እሰናበታችኋለሁ፤ በዚያም ሰዎ
ችም በሙሉ [ለ]ልብሶቼ በእናንተ ደም እን
ዳልተበከሉ ያውቃሉ።
፴፱ እና ከዚያም ኢየሱስን [ሀ]ማየቴን ታው
ቃላችሁ፣ እናም እርሱም [ለ]ፊት ለፊት ተና
ግሮኛል፣ እናም እነዚህን ነገሮች በተመ
ለከተ አንድ ሰው ለሌላ እንደሚናገርም፣
በራሴ ቋንቋ በግልፅ በትህትና ነግሮኛል፤
፵ እናም በፅሁፍ ደካማ በመሆኔም ጥቂ
ቱን ብቻ ፅፌአለሁ።
፵፩ እናም እንግዲህ፣ ነቢያት እና ሐዋ
ሪያት የፃፉለትን ይህንን ኢየሱስን [ሀ]እንድ
ትፈልጉት እመክራችኋለሁ፤ በዚህም የእ
ግዚአብሔር አብ ፀጋ፣ እናም ደግሞ ኢየ
ሱስ ክርስቶስና፣ ስለእነርሱ [ለ]የሚመሰክረው
መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ውስጥና፣ ከእናንተ
ጋር ለዘለዓለም ይኑር። አሜን።

ምዕራፍ ፲፫

ኤተር በዮሴፍ ዘር በአሜሪካ ውስጥ ስለ ምትገነባ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ተናገረ—እርሱም ትንቢትን ተናገረ፤ አስወገዱት፤ የያሬዳውያንን ታሪክ ፃፈ፣ እናም ስለያሬዳውያን መጥፋት አስቀድሞ ተናገረ—በምድሪቱ ሁሉ ላይ ጦርነት አየለ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ እኔ ሞሮኒ፣ የፃፍኩ
ላቸውን ሰዎች ጥፋት በተመለከተ ታሪኬን
ለመጨረስ እቀጥላለሁ።
፪ እነሆ፣ እነርሱም የኤተርን ቃላት
በሙሉ አልተቀበሉም፤ እርሱ ሰው ከተ
ፈጠረ ጊዜ ጀምሮ ሁሉንም ነገሮች በእው
ነት ነግሮአቸዋል፤ እናም ውኃውም ከምድ
ሪቱ ገፅ [ሀ]ከሸሸ በኋላ ከሁሉም መሬት በላይ
የተመረጠች ምድር፣ በጌታ የተመረጠች
ምድር እንደሆነች፤ ስለሆነም ጌታ በዚህች
ምድሪቱ ላይ የሚኖሩት ሰዎች ሁሉ [ለ]እን
ዲያገለግሉት ይፈልጋል፤
፫ እናም ይህም የጌታ ቅዱስ የማምለኪያ
ቦታ፣ ከሰማይም [ሀ]የምትወርደው [ለ]የአዲ
ሲቷ ኢየሩሳሌም ስፍራ እንደነበረችም ነግ
ሮአቸዋል።
፬ እነሆ፣ ኤተር የክርስቶስን ቀናት ተመ
ልክቷል፣ እናም በዚህች ምድር ላይም
[ሀ]ስለአዲሲቷ ኢየሩሳሌምም በተመለከተ
ተናግሯል።
፭ እናም ደግሞ ስለእስራኤል ቤት፣ እናም
[ሀ]ሌሂ ስለመጣበት [ለ]ስለኢየሩሳሌም በተመ
ለከተ ተናግሯል—ጠላቶቹም ከተደመ
ሰሰ በኋላ [ሐ]ቅዱሲቷ ከተማ ለጌታ በድጋሚ
እንደምትገነባ፤ ስለዚህ ኢየሩሳሌም በጥ
ንት ጊዜ የነበረች በመሆኗ አዲሲቷ ኢየ
ሩሳሌም ልትሆን እንደማትችል፤ ነገር ግን
በድጋሚ መገንባት እንደሚገባት፣ እናም
የጌታ ቅዱስ ከተማ እንደምትሆን፤ እናም
ይህችም ለእስራኤል ቤትም እንደምትገነባ
ተናግሯል—
፮ እናም [ሀ]ለዮሴፍ ዘር ቅሪቶችም [ለ]አዲ
ሲቷ ኢየሩሳሌም በዚች ምድር ትገነባለች፣
ለዚህም ነገር [ሐ]ምሳሌ ነበር፤

፴፯ ሀ ት. እና ቃ. ፴፰፥፵፪፤ ፹፰፥፸፬–፸፭፤ ፻፴፭፥፬–፭።
ለ ኤተር ፲፪፥፳፯።
፴፰ ሀ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—ዳኛ።
ለ ያዕቆ. ፩፥፲፱።
፴፱ ሀ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—ክርስቶስ ከሟችነት በኋላ መገለጡ።
ለ ዘፍጥ. ፴፪፥፴፤ ዘፀአ. ፴፫፥፲፩።
፵፩ ሀ ት. እና ቃ. ፹፰፥፷፫፤ ፺፰፥፴፰።
ለ ፫ ኔፊ ፲፩፥፴፪።
፲፫ ፪ ሀ ዘፍጥ. ፯፥፲፩–፳፬፤ ፰፥፫።
ለ ኤተር ፪፥፰።
፫ ሀ ራዕ. ፫፥፲፪፤ ፳፩፥፪።
ለ ፫ ኔፊ ፳፥፳፪፤ ፳፩፥፳–፳፬።
ቅ.መ.መ. አዲሲቱ ኢየሩሳሌም።
፬ ሀ ቅ.መ.መ. ፅዮን።
፭ ሀ ፩ ኔፊ ፩፥፲፰–፳።
ለ ቅ.መ.መ. ኢየሩሳሌም።
ሐ ራዕ. ፳፩፥፲፤ ፫ ኔፊ ፳፥፳፱–፴፮።
፮ ሀ ቅ.መ.መ. ዮሴፍ፣ የያዕቆብ ልጅ።
ለ ት. እና ቃ. ፵፪፥፱፤ ፵፭፥፷፮–፷፯፤ ፹፬፥፪–፭፤ እ.አ. ፩፥፲።
ሐ አልማ ፵፮፥፳፬።
ቅ.መ.መ. ምሳሌዎች።

፯ ዮሴፍ አባቱን ወደ ᵐግብፅ እንዳመጣው
እርሱም በዚያው ሞቷል፤ ስለዚህ ለዮሴፍ
አባት እንዳይጠፋ መሃሪ እንደሆነለት ሁሉ
የዮሴፍ ዘርም ᵃእንዳይጠፋ መሃሪ ለመሆን፣
ጌታ የዮሴፍን ዘር ቅሪት ከኢየሩሳሌም አስ
ወጥቷል።

፰ ስለዚህ፣ የዮሴፍ ቤት ቅሪት በዚህ
ᵐምድር ላይ ይገነባሉ፤ ይህችም ለእነርሱ
የውርስ ምድር ትሆናለች፤ እናም እንደ
ጥንቷ ኢየሩሳሌምም ቅዱስ ከተማ ለጌታ
ይገነባሉ፤ እናም ምድር እስከምታልፍ
መጨረሻዋ እስከሚሆን ድረስ ᵃከእንግዲህ
ወዲህ አይቀላቀሉም።

፱ እናም ᵐአዲስ ሰማይ እና አዲስ ምድር
ይኖራል፤ እናም የጥንቶቹ ከማለፋቸው
በስተቀር እንደ ጥንቱ ይሆናሉ፣ እናም
ሁሉም ነገሮች አዲስ ሆነዋል።

፲ እናም አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ትመሰረ
ታለች፤ እናም በእርሷም የሚኖሩባት የተ
ባረኩ ይሆናሉ፤ ምክንያቱም በበጉ ደም
ልብሳቸው ᵐየነፃው እነርሱ ናቸውና፤ እናም
እነርሱም ከእስራኤል ቤት ከነበሩት ከዮሴፍ
ዘር ቅሪት ጋር ተቆጥረዋልና።

፲፩ እናም ደግሞ የጥንቷ ኢየሩሳሌም
ትመሰረታለች፤ እናም በውስጧ የሚ
ኖሩትም የተባረኩ ናቸው፣ በበጉ ደም
ታጥበዋልና፤ እናም እነርሱም ነበሩ ተበ
ትነው የነበሩት፣ እናም በምድሪቷ በአራ
ቱም ማዕዘናት፣ እናም ከሃገሪቱ ᵐከበስተ
ሰሜን በኩል ᵃየተሰባሰቡት፣ እናም እግ
ዚአብሔር ከአባታቸው ᶜከአብርሃም ጋር
የገባውን የቃል ኪዳን በረከት ተካፋዮች
የሆኑት።

፲፪ እናም እነዚህ ነገሮች በሚመጡበት
ጊዜ እንዲህ የሚሉት ቅዱሳን መፃህፍት
ይፈጸማሉ፥ መጨረሻ የሚሆኑት ᵐበመጀ
መሪያ የነበሩት ነበሩ፤ እናም በመጨረሻ
የነበሩት መጀመሪያ የሚሆኑም ነበሩ።

፲፫ እናም ከዚህ የበለጠን ልጽፍ ነበር፣
ነገር ግን ተከልክያለሁ፤ ነገር ግን የኤተር
ትንቢቶች ታላቅና አስደናቂዎች ነበሩ፤
ነገር ግን ምንም የማይረባ አድርገው ቆጠ
ሩት እናም አውጥተው ጣሉት፤ እናም በቀ
ንም እራሱን በድንጋይ ዋሻ ደበቀ፣ እናም
በምሽት በመሄድ ለህዝቡ መሆን ስለሚገባ
ቸው ነገሮች ይመለከታል።

፲፬ እናም በድንጋይ ዋሻ ውስጥ በተቀ
መጠ ጊዜ በምሽት በህዝቡ ላይ የሚመጣ
ውን ጥፋት በመመልከት የሚቀሩትን የዚ
ህን ታሪክ ቃል ፃፈ።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ እርሱንም ከህዝቡ
መካከል ባስወጡበት ዓመት በህዝቡ መካ
ከል ታላቅ ጦርነት ተጀመረ፣ ምክንያቱም
የተነሳሱ ኃያላን የሆኑ እናም ይነገሩ በነበ
ሩት ሚስጢራዊ የክፋት እቅዳቸውም ቆሪ
ያንተመርን ለማጥፋት የፈለጉ ብዙ ሰዎች
ነበሩና።

፲፮ እናም እንግዲህ የጦርነትን ጥበብ
እናም የዓለምን ማጭበርበር ሁሉ ቆሪያን
ተመር ከአጠና በኋላ፣ ስለዚህ ሊገድሉት
ከፈለጉት ጋር ተዋጋ።

፲፯ ነገር ግን መልከ መልካም የሆኑት
የቆሆር ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ልጆቹ እንዲ
ሁም እርሱም ንሰሃ አልገቡም፤ የቆሪሆርም
መልከ መልካም ወንዶችና ሴቶች ልጆቹ
ንሰሃ አልገቡም፤ እናም በአጠቃላይ መልከ
መልካም ከሆኑት በምድሪቱ ሁሉ ላይ ካሉት
ወንዶች እና ሴቶች ልጆች ማንም ንሰሃ የገባ
አልነበረም።

፲፰ ስለሆነም፣ እንዲህ ሆነ ኤተር በድን
ጋይ ዋሻ በኖረበት በመጀመሪያው አመት፣
መንግስቱን ያገኙ ዘንድ ከቆሪያንተመር ላይ

፯ ᵃ ዘፍጥ. ፴፮፡፪–፯፣ ፴፯፡፲፯።
ᵇ ᵃ ኔፊ ፫፡፭።
፰ ᵃ ቅ.መ.መ. የቃል ኪዳን
ምድር።
ᵇ ᵃ ሞሮኒ ፲፡፴፭።
፱ ᵃ ᵇ ዴዋ. ፫፡፲–፲፫፣
ራዕ. ፳፩፡፩፣
ᵇ ᵃ ኔፊ ፳፯፡፫፣
ት. እና ቃ. ፲፩፡፳፫–፳፭።
፲ ᵃ ራዕ. ፯፡፲፣
ᵇ ᵃ ኔፊ ፲፪፡፲–፲፩፣
አልማ ፭፡፳፯።
፲፩ ᵃ ት. እና ቃ. ፲፴፫፡፳፯–፴፭።
ᵇ ᵃ ቅ.መ.መ. እስራኤል—
የእስራኤል መሰብሰብ።
ᶜ ቅ.መ.መ. የአብርሐም ቃል
ኪዳን።
፲፪ ᵃ ማር. ፲፡፴፩፣
ᵇ ᵃ ኔፊ ፲፫፡፴፪፣
ያዕቆ. ፭፡፳፫፣
ት. እና ቃ. ፯፡፱።

በሚዋጉት ᵐበሚስጢራዊው ሴራዎች በጎ
ራዴ የተገደሉ ብዙ ሰዎች ነበሩ።
፲፱ እናም እንዲህ ሆነ የቆሪያንተመር ልጆ
ችም ብዙ ተዋጉ፣ ብዙም ደም ፈሰሳቸው።
፳ እናም በሁለተኛው ዓመት ወደ ᵐቆሪ
ያንተመር እንዲሔድ እና እርሱ እና ቤተ
ሰዎቹም በሙሉ ንሰሃ ከገቡ ጌታ ለእርሱ
መንግስቱን እንደሚሰጠው ህዝቡንም እን
ደሚያድን በመናገር እንዲተነብይ የጌታ
ቃል ለኤተር መጣ—
፳፩ አለበለዚያ ግን ይጠፋሉ፣ እናም ከእ
ርሱ በስተቀር ቤተሰዎቹ በሙሉ ይጠፋሉ።
እናም እርሱም ᵐሌሎች ህዝቦች ምድሪቱን
ለውርስ እንደሚቀበሉ የተነገረውን ትንቢት
በተመለከተ ሲፈፀም እንዲያይ ብቻ በህ
ይወት ይቆያል፤ እናም ᵃቆሪያንተመርም
በእነርሱ ይቀበራል፤ እናም ከቆሪያንተመር
በስተቀር እያንዳንዱ ነፍስም ይጠፋል።
፳፪ እናም እንዲህ ሆነ ቆሪያንተመርም፣
ቤተሰዎቹም፣ እንዲሁ ህዝቡ ንሰሃ አልገ
ቡም፤ እናም ጦርነቱም አልቆመም፤ እነ
ርሱም ኤተርን ለመግደል ፈለጉ፣ ነገር ግን
እርሱ ሸሸ፣ እናም በድንጋይ ዋሻ ውስጥ
በድጋሚ ራሱን ደበቀ።
፳፫ እናም እንዲህ ሆነ ሻረድ ተነሳ፣ እር
ሱም ደግሞ ከቆሪያንተመር ጋር ተዋጋ፤
እናም አሸነፈው፣ በሦስተኛውም ዓመት
ወደ ግዞት አስገባው።
፳፬ እናም የቆሪያንተመር ወንድ ልጆች
በአራተኛው ዓመት ሻረድን አሸነፉት፣
እናም በድጋሚ ለአባታቸው መንግስትን
አስገኙ።
፳፭ እንግዲህ በምድሪቱ ሁሉ ላይ ጦር
ነት ተጀመረ፤ እያንዳንዱ ሰው ከቡድኑ ጋር
በመሆን ለሚፈልገው ነገር ተዋጋ።
፳፮ እናም ዘራፊዎች ነበሩ፤ እናም በአጠ
ቃላይ በምድሪቱ ላይ ሁሉም ዓይነት ክፋ
ቶች ነበሩ።
፳፯ እናም እንዲህ ሆነ ቆሪያንተመር
በሻረድ እጅግ ተቆጥቶ ነበር፤ እናም በድ
ጋሚም ከእርሱ ጋር ለመዋጋት ከጦሩ ጋር
ሄደ፤ እናም እነርሱም በታላቅ ቁጣ ተገ
ናኙ፤ እናም በጊልጋል ሸለቆም ተገናኙ፤
እናም ጦርነቱም እጅግ የከፋ ነበር።
፳፰ እናም እንዲህ ሆነ ሻረድ ከእርሱ ጋር
ለሦስት ቀናት ተዋጋ። እናም እንዲህ ሆነ
ቆሪያንተመር አሸነፈው፣ እናም በሔሽ
ሎን ሜዳ እስከሚመጣም ድረስ አሳደደው።
፳፱ እናም እንዲህ ሆነ በሜዳማው ቦታም
ሻረድ ተዋጋው፤ እናም ቆሪያንተመርን
አሸነፈው፣ እናም መልሶ ወደ ጊልጋል
ሸለቆ አሳደደው።
፴ እናም ቆሪያንተመር በጊልጋል ሸለቆ
በድጋሚ ከሻረድ ጋር ተዋጋ፣ እናም በዚ
ያም ሻረድን አሸነፈው እናም ገደለው።
፴፩ እናም ሻረድም ቆሪያንተመርን ጭኑ
ላይ አቆሰለው፤ እርሱም ለሁለት ዓመታት
በድጋሚ ወደ ጦርነቱ አልተመለሰም ነበር፤
በዚህም ጊዜ በምድሪቱ ላይ የነበሩት ሰዎች
ሁሉ የደም መፋሰስ ያደርጉ ነበር፣ እናም
እነርሱንም የሚያቆማቸው ማንም አልነ
በረም።

ምዕራፍ ፲፡

የህዝቡ ክፋት በምድሪቱ ላይ እርግማን ያመጣል—ቆሪያንተመር ከጊልአድ፣ ከዚያም ከሊብ፣ እናም ቀጥሎ ከሺዝ ጋር ጦርነትን አደረገ—ደም እና እልቂት ምድሪቱን ሸፈነ።

፩ እናም እንግዲህ በህዝቡም ክፋት የተ
ነሳ በምድሪቱ ሁሉ ላይ ታላቅ ᵐእርግማን
ሆነ፤ በዚህም አንድ ሰው መሳሪያውን ወይ
ንም ጎራዴውን በራሱ መደርደሪያ ካስቀ
መጠ፣ ወይንም ማስቀመጥ በሚችልበት
ስፍራ ካደረገ፣ እነሆ፣ በሚቀጥለው ቀን
አያገኘውም፣ ስለዚህ እርግማኑ በምድሪቱ
ላይ ታላቅ ሆኗልና።

፲፯ ᵐ ኤተር ፰ ፡ ፱–፳፯።
፳ ᵐ ኤተር ፲፪ ፡ ፩–፪።
፳፩ ᵐ ኦምኒ ፩ ፡ ፲፱–፳፩፤ ኤተር ፲፩ ፡ ፳፩።
ᵃ ኤተር ፲፩ ፡ ፳፱–፴፪።
፲፡ ᵐ ሔለ. ፲፪ ፡ ፲፯፤ ፲፡ ፡ ፲፯–፲፰፤ ሞር. ፩ ፡ ፲፯–፲፯፤ ፪ ፡ ፲–፲፡።

፪ ስለዚህ እያንዳንዱ የራሱ የሆነውን በእጁ አጥብቆ ይይዛል፣ እናም ለሌላ አያ በድርም እንዲሁም ከሌላም አይበደርም፤ እናም እያንዳንዱ ሰው ንብረቱን፣ እናም ህይወቱን፣ እናም የሚስቱን እናም የልጁን ህይወት ለመጠበቅ የጎራዴውን እጀታ በቀኝ እጁ ይይዛል።

፫ እናም እንግዲህ ከሁለት ዓመት በኋላ፣ እናም ሻረድ ከሞተም በኋላ፣ እነሆ፣ የሻረድ ወንድም ተነሳ፣ እናም ከቆሪያንተመር ጋር ተዋጋ፣ በዚህም ቆሪያንተመርም አሸነፈው እናም ወደ አኪሽ ምድረበዳም አሳደደው።

፬ እናም እንዲህ ሆነ የሻረድ ወንድም በአ ኪሽ ምድረበዳ ውስጥ ከእርሱ ጋር ተዋጋ፤ እናም ጦርነቱም እጅግ የከፋ ነበር፣ እናም ብዙ ሺዎችም በጎራዴው ወደቁ።

፭ እናም እንዲህ ሆነ ቆሪያንተመር ምድ ረበዳውን ከበበ፤ እናም የሻረድ ወንድም በምሽት ከምድረበዳው ሄደ እናም የሰከ ሩትን የቆሪያንተመርን ወታደሮች በከፊል ገደሉአቸው።

፮ እናም ወደ ሞሮን ምድር ሔደ፣ እናም እራሱን በቆሪያንተመር ዙፋን አስቀመጠ።

፯ እናም እንዲህ ሆነ ቆሪያንተመር ለሁ ለት ዓመታት ከወታደሮቹ ጋር በምድ ረበዳው ኖረ፤ በዚያም ሥፍራ ለወታደ ሮቹ ጥንካሬ ተቀበለ።

፰ እንግዲህ የሻረድ ወንድም ጊልአድ የሚባለው ደግሞ በሚስጢራዊ ሴራዎች የተነሳ ለሠራዊቱ ብርታትን አገኘ።

፱ እናም እንዲህ ሆነ በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ሳለ ሊቀ ካህኑ ገደለው።

፲ እናም እንዲህ ሆነ ከሚስጢራዊ ሴራ ዎች አንዱ በሚስጢራዊው መተላለፊያ ቦታ ውስጥ ገደለው፣ እናም መንግስቱን ለራሱ አደረገ፤ እናም ስሙም ሊብ ይባል ነበር፤ እናም ሊብም ከህዝቡ ሁሉ ሰዎች መካከል በላይ ጠንካራ አቋም የነበረው ሰው ነበር።

፲፩ እናም እንዲህ ሆነ በሊብ የመጀመሪያ ዓመት፣ ቆሪያንተመር ወደ ሞሮን ምድር መጣ፣ እናም ከሊብ ጋር ተዋጋ።

፲፪ እናም እንዲህ ሆነ ከሊብም ጋር ተዋጋ፤ ሊብም በእጁ ላይ መትቶ አቆሰ ለው፤ ይሁን እንጂ፣ የቆሪያንተመር ሠራ ዊቶች ሊብን ገፉት፣ እርሱም በባህሩ ዳርቻ ወደ ወሰኑ ሸሸ።

፲፫ እናም እንዲህ ሆነ ቆሪያንተመር ተከ ተለው፤ እናም ሊብም በባህሩ ዳርቻ ከእ ርሱ ጋር ተዋጋ።

፲፬ እናም እንዲህ ሆነ ሊብ የቆሪያንተመ ርን ወታደሮች መታቸው፣ እነርሱም በድ ጋሚ ወደ አኪሽ ምድረበዳ ሸሹ።

፲፭ እናም እንዲህ ሆነ እርሱ ወደ አጎሽ መስክ እስከሚመጣ ድረስ ሊብ ተከተለው። እናም ቆሪያንተመር ከሊብ በፊት ሲሸሽም በምድሯ በዚያ ክፍል የነበሩትን ህዝቦች በሙሉ ይዞ ሄዶ ነበር።

፲፮ እናም ወደ አጎሽ መስክ በመጣም ጊዜ ከሊብ ጋር ተዋጋ፣ እናም እስከሚሞት ድረ ስም መታው፤ ይሁን እንጂ፣ የሊብ ወን ድም በቆሪያንተመር ላይ በምትኩ መጣ በት፣ እናም ጦርነቱም እጅግ የከፋ ሆነ፤ በዚህም ቆሪያንተመር በድጋሚ ከሊብ ወን ድም ሠራዊት ፊት ሸሸ።

፲፯ እናም የሊብ ወንድም ስሙ ሺዝ ይባል ነበር። እናም እንዲህ ሆነ ሺዝ ቆሪያንተመ ርን አሳደደው፣ እናም ብዙ ከተሞችንም ድል አደረገ፣ እናም ሴቶችን እና ልጆችን ገደለ፣ እና ከተሞችንም አቃጠለ።

፲፰ እናም በምድሪቱ ሁሉ ላይ ሺዝ ተፈራ፤ አዎን፣ በምድሪቱ ሁሉ ጨኸት ሆነ—የሺዝን ሠራዊት ማን ሊቋቋም ይቻ ለዋል? እነሆ፣ የምድሪቱ ገፅ በፊቱ ጠረ ጋት!

፲፱ እናም እንዲህ ሆነ በምድሪቱ ሁሉ ላይም ህዝቡ ከሠራዊቱ ጋር በአንድነት ተሰባሰበ።

፳ እናም እነርሱም የተከፋፈሉ ነበሩ፤ እናም ግማሹ ወደ ሺዝ ወታደሮች ሸሹ፤ ግማሹ ወደ ቆሪያንተመር ወታደሮች ሸሹ።

፳፩ እናም ጦርነቱ እጅግ ታላቅ እና ረጅም ስለነበር፣ እናም ደም መፋሰሱ እና እልቂቱ እይታም እጅግ ለረጅም ጊዜ ስለ

ነበር፣ ምድሪቱም ገጽታዋ በሙሉ "በሙ
ታን ተሸፍኖ ነበር።

፳፪ እናም ፈጣን ጦርነት ስለነበር ሙታንን
ለመቅበር የቀረ ማንም አልነበረም፣ ነገር
ግን የወንዶችን፣ የሴቶችን፣ እና የልጆችን
ሙታኖቻቸውን በምድር ገፅ ላይ እንደተዘ
ረጉ፣ ለስጋ "ትል ምግብ እንዲሆኑ በመተው
ከደም ማፋሰስ ወደ ደም ማፋሰስ ዘመቱ።

፳፫ እናም የዚህ ሽታም በምድሪቱ ሁሉ
ላይ፣ እንዲሁም በምድሩ ገጽ ላይ ሁሉ
ሆነ፤ ስለዚህ ህዝቡ በሽታው ምክንያት በም
ሽት ሆነ እንዲሁም በቀን ተቸግረው ነበር።

፳፬ ይሁን እንጂ፣ ሺዝ ቆሪያንተመርን
ማሳደዱን አልተወም፤ የተገደለውን የወን
ድሙን ደም በቆሪያንተመር ላይ ለመበቀል፣
እናም ጌታ ቆሪያንተመር በጎራዴ እንደማይ
ሞት ለኤተር ነግሮት በነበረው ቃል ላይ ለመ
በቀል፣ በመሃላ እራሱን አነሳስቶ ነበርና።

፳፭ እናም በቁጣው ሙላት ጌታ እንደጎ
በኛቸው፣ እናም ክፋቶቻቸው እና እርኩ
ሰቶቻቸው ለዘላለማዊው ጥፋታቸው መን
ገድ እንዳዘጋጁ እንመለከታለን።

፳፮ እናም እንዲህ ሆነ ሺዝ ቆሪያንተመ
ርን በስተምስራቅ በኩል እስከባህሩ ዳርቻ
ወሰን አሳደደው፣ እናም ለሦስት ቀናትም
ከሺዝ ጋር ተዋጋ።

፳፯ እናም በሺዝ ወታደሮች መካከል
ጥፋቱ አሰቃቂ ስለነበር ህዝቡ መፍራት
ጀመሩ፣ እናም ከቆሪያንተመር ወታደሮች
ፊት መሸሽ ጀመሩ፤ እናም ወደ ቆሪሆር
ምድር ሸሹ፣ እናም በፊታቸው የነበሩትን
ነዋሪዎች ከእነርሱ ጋር ያልተቀላቀሉትን
በሙሉ ጠረጉአቸው።

፳፰ እናም በቆሪሆር ሸለቆ ውስጥ ድን
ኳናቸውን ተከሉ፤ እናም ቆሪያንተመ
ርም ድንኳኑን በሹር ሸለቆ ተከለ። እንግ
ዲህ የሹር ሸለቆ ከቆምኖር ኮረብታ አጠገብ
ነበር፤ ስለዚህ፣ ቆሪያንተመር ወታደሮቹን
በቆምኖር ኮረብታ ላይ በአንድነት ሰበሰባ
ቸው፣ እናም የሺዝን ወታደሮች ለጦርነት
ለመጋበዝ መለከትን ነፋ።

፳፱ እናም እንዲህ ሆነ እነርሱም መጡ፣
ነገር ግን በድጋሚ ወደ ኋላ አባረሩአቸው፤
እናም ለሁለተኛ ጊዜ መጡ፤ እናም ለሁ
ለተኛ ጊዜም ተባረሩ። እናም እንዲህ ሆነ
ለሦስተኛ ጊዜ በድጋሚ መጡ፤ እናም ጦር
ነቱም እጅግ የከፋ ሆነ።

፴ እናም እንዲህ ሆነ ሺዝም ቆሪያንተመ
ርን መትቶ በበርካታ ቦታዎች ላይ አቆሰ
ለው፤ እናም ቆሪያንተመር ደም ስለፈሰ
ሰው እራሱን ሳተ፣ እናም የሞተም ይመ
ስል ስለነበር በሽከማ ተወሰደ።

፴፩ እንግዲህ በሁለቱም በኩል የሞቱት
ወንዶች፣ ሴቶችና ልጆች ብዙ ስለነበሩ፣
ሺዝ ወታደሮቹ የቆሪያንተመርን ወታደሮች
እንዳያባርሩአቸው አዘዘ፤ ስለዚህ እነርሱም
ወደ ጦር ሰፈራቸው ተመለሱ።

ምዕራፍ ፲፭

በሚሊዮን የሚቆጠሩ ያሬዳውያን በጦር ነቱ ሞቱ—ሺዝ እና ቆሪያንተመር ህዝ ቡን በአንድነት ለመገዳደል ሰበሰቡ—የጌ ታም መንፈስ ከእነርሱ ጋር መሆ ኑን አቆመ—የያሬዳውያን ሀገር ፈጽማ ጠፋች—ቆሪያንተመር ብቻ ቀረ።

፩ እናም እንዲህ ሆነ ቆሪያንተመር ቁስሉ
እንደዳነለት፣ ኤተር ለእርሱ የተናገራቸ
ውን "ቃላት ማስታወስ ጀመረ።

፪ ከህዝቦቹም ወደ ሁለት ሚሊዮን የሚ
ጠጉት በጎራዴው እንደተገደሉ ተመ
ለከተ፣ እናም በልቡም ማዘን ጀመረ፤
አዎን፣ ሁለት ሚሊዮን ኃያላን ሰዎች፣
እናም ደግሞ ሚስቶቻቸው እና ልጆቻቸ
ውም ጭምር ተገድለው ነበር።

፫ ለሰራቸውም ክፋቶች ንሰሃ መግ
ባት ጀመረ፤ ሁሉንም በነቢያት አንደበት
የተነገሩትን ቃላቶች ማስታወስ ጀመረ፤
እናም እያንዳንዱም የተናገሩአቸው እን
ደተፈፀሙ ተመለከተ፤ እናም ነፍሱ አዘነች
እናም መፅናናትን ለመቀበል አልቻለም።

፬ እናም እንዲህ ሆነ ሺዝ ህዝቡን እንዲ

ያድንለት፣ እናም ለህዝቡም ህይወት ሲል መንግስቱን እንደሚሰጠው በመፈለግ ደብ ዳቤ ፃፈለት።

፮ እናም እንዲህ ሆነ ሺዝ ደብዳቤውን ሲቀበል ለቆሪያንተመር ራሱን የሰጠ እን ደሆን በራሱ ጎራዴ እንደሚገድለው እናም የህዝቡንም ህይወት እንደሚያተርፍ ደብ ዳቤን ፃፈለት።

፯ እናም እንዲህ ሆነ ህዝቡም ለክፋታቸው ንሰሃ አልገቡም፤ እናም የቆሪያንተመር ህዝ ቦች በሺዝ ህዝቦች በቁጣ ተነሳስተው ነበር፤ እናም የሺዝ ህዝብም በቆሪያንተመር ህዝቦች ላይ በቁጣ ተነሳስተው ነበር፤ ስለዚህ የሺዝ ህዝቦች ከቆሪያንተመር ህዝቦች ጋር ተዋጉ።

፰ እናም ቆሪያንተመርም ሊሸነፍ እንደ ተቃረበ በተመለከተ ጊዜ በድጋሚ ከሺዝ ሰዎች ፊት ሸሸ።

፱ እናም እንዲህ ሆነ ቆሪያንተመርም ትርጓሜውም ትልቅ፣ ወይንም ከሁሉም የሚበልጥ ማለት ወደሆነው ወደ ሪፕሊአን ኩም ውኃ መጣ፤ ስለዚህ፣ ወደዚህ ውኃ በመጡ ጊዜ ድንኳናቸውን ተከሉ፤ እናም ደግሞ ሺዝ ድንኳኑን በእነርሱ አጠገብ ተከለ፤ እናም ከዚያም በሚቀጥለው ቀን ለውጊያ መጡ።

፲ እናም እንዲህ ሆነ እጅግ የከፋ ውጊ ያን አደረጉ፤ በዚያም ቆሪያንተመር በድ ጋሚ ቆሰለ፣ እናም ብዙም ደም ስለፈሰሰው እራሱን በመሳት ወደቀ።

፲፩ እናም እንዲህ ሆነ የቆሪያንተመር ወታ ደሮች የሺዝን ወታደሮች በኃይል አጠቁአ ቸው፣ ስለዚህ አሸነፉአቸው፣ እናም ከፊ ታቸውም እንዲሸሹ አደረጉአቸው፤ እናም እነርሱም በስተደቡብ በኩል ሸሹ፣ እናም አጋዝ ተብሎ በሚጠራም ስፍራ ድንኳና ቸውን ተከሉ።

፲፪ እናም እንዲህ ሆነ የቆሪያንተመር ወታደሮችም በራማህ ኮረብታ ድንኳኖቻ ቸውን ተከሉ፤ እናም በዚያን ኮረብታ ነበር አባቴ ሞርሞን ቅዱስ የሆነውን መዛግብት ለጌታ ᵘየደበቀው።

፲፫ እናም እንዲህ ሆነ ከኤተር በስተቀር ከሞት የተረፉትን ሰዎች በሙሉ በአንድ ላይ በምድሪቱ ላይ ሰበሰቡአቸው።

፲፬ እናም እንዲህ ሆነ ኤተር የህዝቡን ሥራ ሁሉ ተመለከተ፤ እናም በቆሪያንተ መር በኩል የነበሩትም ሰዎችም ከቆሪያን ተመር ወታደሮች ጋር በአንድነት ተሰባስ በው እንደነበር ተመለከተ፤ እናም በሺዝ በኩል የነበሩትም ሰዎችም በሺዝ ወታደ ሮች በኩል በአንድ ላይ ተሰባስበው ነበር።

፲፭ ስለሆነም፣ እናም በምድሪቷ ፊት ላይ የነበሩትን ሁሉ ያገኙ ዘንድ፣ እናም ለመ ቀበል የሚችሉትን ጥንካሬዎች ሁሉ ለመ ቀበል፣ ህዝቡን ለዓራት አመታት ሰበሰቡ አቸው።

፲፮ እናም እንዲህ ሆነ ሁሉም እያንዳ ንዳቸው ከነሚስቶቻቸው፣ እናም ከነል ጆቻቸው ከፈለጉት ወታደሮች ጋር በተ ሰበሰቡበት ጊዜ—ወንዶች፣ ሴቶች እና ልጆች የጦር መሳሪያ በመታጠቅ፤ ጋሻዎ ችን፣ እናም ᵘየደረት ኪሶችን፣ እናም ኮፍ ያን በመታጠቅ፣ እናም ማንኛውንም ዓይ ነት የጦር አልባሳትን በመልበስ—እያን ዳንዱም ከሌላው ጋር ለመዋጋት ዘመቱ፤ እናም ቀኑን ሙሉ ተዋጉ፣ ሆኖም ግን አላሸነፉም።

፲፯ እናም እንዲህ ሆነ ምሽት በሆነም ጊዜ ደክመው ነበር፣ እናም ወደ ጦር ሰፈራቸ ውም ተመለሱ፤ እናም ወደ ጦር ሰፈራቸ ውም ከተመለሱ በኋላ፣ ለሞቱት ወገኖቻ ቸው ይጮኹ፣ እንዲሁም ያለቅሱ ነበር፤ እናም ጩኸታቸው እናም ለቅሶአቸውታ ላቅ በመሆኑ አየሩን እጅግ የሚሰነጥቅ ታላቅ ኃይል ነበረው።

፲፰ እናም እንዲህ ሆነ በሚቀጥለውም ቀን ዳግም ለውጊያ ሄዱ፣ እናም ያም ቀን ታላቅና አስፈሪ ነበር፤ ይሁን እንጂ አላሸ ነፉም፣ እናም በድጋሚ ምሽት በሆነበት ጊዜም ህዝቦቻቸው ስለሞቱባቸው አካባ ቢውን በጨኸትና በልቅሶ ረበሹት።

፲፱ እናም እንዲህ ሆነ ቆሪያንተመርም

ᵘ ሞር. ፯፡፮። ᵘ ሞዛያ ፰፡፭–፲።

በድጋሚ ለውጊያ ወደእርሱ እንዳይመጣ፣ ነገር ግን መንግስቱን እንዲይዝ፣ እናም የህ ዝቡን ህይወት እንዲያተርፍለት በመጠየቅ ለሺዝ ደብዳቤ በድጋሚ ፃፈለት።

፲፱ ነገር ግን እነሆ፣ የጌታ መንፈስ ከእነ ርሱ ጋር መሆኑን አቆመ፣ እናም ᐸሰይጣ ንም በሰዎች ልብ ሙሉ ስልጣን ነበረው፤ ልባቸውን በማጠጠራቸው፣ አዕምሮአቸ ውን በማሳወራቸው እንዲጠፉ ዘንድ ተስፋ ቆርጠው ነበርና፤ ስለሆነም በድጋሚ ወደ ጦርነት ሄዱ።

፳ እናም እንዲህ ሆነ በዚያን ቀን በሙሉ ተዋጉ፤ እናም ምሽት ሲሆን ጎራዴአቸውን ይዘው ተኙ።

፳፩ እናም በሚቀጥለው ቀንም ምሽት እስ ከሚሆን ድረስ ተዋጉ።

፳፪ እናም ምሽቱ ሲመጣ ልክ ወይን ጠጥቶ እንደሰከረ ሰው በቁጣ ᐸሰክረው ነበር፤ እናም ጎራዴአቸውን ይዘው በድ ጋሚ ተኙ።

፳፫ እናም በሚቀጥለው ቀን በድጋሚ ተዋጉ፤ እናም ምሽቱም በመጣም ጊዜ ከቆሪያንተመር ሰዎች ከሃምሳ ሁለቱ እናም ከሺዝ ሰዎች ስልሳ ዘጠኙ በስተቀር በጎራዴ ተመትተው ወደቁ።

፳፬ እናም እንዲህ ሆነ በዚያን ምሽትም ጎራዴአቸውን እንደያዙ ተኙ፣ እናም በሚ ቀጥለው ቀን በድጋሚ ተዋጉ፣ እናም ቀኑን ሙሉ በኃይል፣ በጎራዴአቸው እና በጋሻ ዎቻቸው ተዋጉ።

፳፭ እናም ምሽት በሆነም ጊዜ ሠላሳ ሁለት የሺዝ ሰዎች፣ እንዲሁም ሃያ ሰባት የቆሪያንተመር ሰዎች ብቻ ነበሩ።

፳፮ እናም እንዲህ ሆነ ምግባቸውን በል ተው ተኙ፣ እናም በሚቀጥለውም ቀን ለሞት ተዘጋጁ። እናም እነርሱም እንደ ሰዎች ጥንካሬ ትላልቅ እና ኃያላን ሰዎች ነበሩ።

፳፯ እናም እንዲህ ሆነ ለሦስት ሰዓታትም ተዋጉ፣ እናም ደም ስለፈሰሳቸው እራሳቸ ውን ሳቱ።

፳፰ እናም እንዲህ ሆነ የቆሪያንተመር ሰዎች ለመራመድ የሚያስችላቸውን በቂ ብርታት ባገኙ ጊዜ ህይወታቸውን ለማ ትረፍ ሊሸሹ ነበር፤ ነገር ግን እነሆ ሺዝ ተነሳ፣ እናም ደግሞ የእርሱ ሰዎች ተነሱ፣ እናም ቆሪያንተመርን ለመግደል አለበለ ዚያም በጎራዴው እንደሚጠፉ በቁጣው ማለ።

፳፱ ስለሆነም፣ እነርሱን ተከተላቸው፣ እናም በሚቀጥለው ቀን ደረሰባቸው፤ እናም በድጋሚ በጎራዴ ተዋጉ። እናም እንዲህ ሆነ ከቆሪያንተመር እና ከሺዝ በስተቀር ᐸሁሉም በጎራዴው በወደቁ ጊዜ፣ እነሆ፣ ሺዝ ደም ስለፈሰሰው እራሱን ስቶ ነበር።

፴ እናም እንዲህ ሆነ ቆሪያንተመር ጎራ ዴውን በመመርኮዝ ለጊዜ ትንሽ አረፈ፣ እናም የሺዝን እራስ ቆረጠ።

፴፩ እናም እንዲህ ሆነ የሺዝን ራስ በመ ምታት ከቆረጠ በኋላ፣ ሺዝ በእጆቹ በመ መርኮዝ ተነሳ፣ እናም ወደቀ፤ እናም ለመ ተንፈስ ከታገለም በኋላ ሞተ።

፴፪ እናም እንዲህ ሆነ ᐸቆሪያንተመር በመሬቱ ላይ ወደቀ፣ እናም ህይወት የሌ ለውም መሰለ።

፴፫ እናም ጌታ ኤተርን ተናገረው፤ እናም እንዲህ አለው፥ ወደፊት ሂድ። እናም እር ሱም ወደ ፊት ሄደ፣ እናም የጌታ ቃል በሙሉ መፈፀሙንም ተመለከተ፤ እናም ᐸታሪኩንም ጨረሰ፤ (እኔም መቶኛውን ክፍል አልፃፍኩም) እናም የሊምሂ ሰዎች እንዲያገኙት በማድረግም ደበቀው።

፴፬ እንግዲህ ᐸበኤተር የተፃፉት የመጨ ረሻዎቹ ቃላት እነዚህ ናቸው፥ ጌታ እኔ እንድቀየር ከፈቀደ ወይንም በስጋ የጌታን ፈቃድ እንድፈጽም ቢያደርግ፣ እኔ በእግ ዚአብሔር መንግስት የምድን ከሆነ ሌላው ምንም አይደለም። አሜን።

፲፱ ᐸ ቅ.መ. ዲያብሎስ።
፳፪ ᐸ ሞሮኒ ፱፡፳፫።
፳፱ ᐸ ኤተር ፲፫፡፳–፳፩።
፴፪ ᐸ ኦምኒ ፩፡፳–፳፪።
፴፫ ᐸ ሞዛያ ፳፡፱፤ አልማ ፴፯፡፳፩–፴፩፤ ኤተር ፩፡፩–፫።
፴፬ ᐸ ኤተር ፲፪፡፪።

መፅሐፈ ሞሮኒ

ምዕራፍ ፩

ሞሮኒ ለላማናውያን ጥቅም ፃፈ—ክርስቶስን ያልካዱ ኔፋውያን ተገደሉ። ፬፻፩–፬፻፳፩ ዓ.ም. ገደማ።

እንግዲህ እኔ [ሀ]ሞሮኒ፣ የያሬዳውያንን ሰዎች ታሪክ አሳጥሮ መጻፉን ከጨረስኩ በኋላ፣ ከዚህ የበለጠ እፅፋለሁ ብዬ አላሰብኩም ነበር፤ ነገር ግን እስካሁንም አልጠፋሁም፤ እናም ላማናውያን ያጠፉኛል ብዬ በመፍራቴ ራሴን አላሳወቅሁም።

፪ እነሆም፣ በመካከላቸው ያሉት [ሀ]ጦርነቶችም እጅግ ኃይለኛ ናቸው፤ እናም በጥላቻቸው ምክንያትም ክርስቶስን የማይክዱትን ኔፋውያን እያንዳንዳቸውን [ለ]ይገድላሉ።

፫ እናም እኔ፣ ሞሮኒ፣ ክርስቶስን [ሀ]አልክደውም፤ ስለዚህ ለህይወቴ ደህንነትም ስል በምችለው ቦታ ሁሉ እዘዋወራለሁ።

፬ ስለዚህ ከገመትኩት ተቃራኒ የሆኑ ጥቂት ነገሮችን እፅፋለሁ፤ ከዚህ የበለጠ እንድፅፍ አልጠብቅም ነበርና፤ ነገር ግን በጌታ ፈቃድ ወደፊት አንድ ቀን ለወንድሞቼ ለላማናውያን ምናልባት ይጠቅማቸው ዘንድ ከዚህ የበለጠ ጥቂት ነገሮችን እጽፋለሁ።

ምዕራፍ ፪

ኢየሱስም ኔፋውያን ደቀመዛሙርት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን እንዲሰጡ ስልጣንን ሰጣቸው። ፬፻፩–፬፻፳፩ ዓ.ም. ገደማ።

፩ ክርስቶስ ለመረጣቸው አስራ ሁለቱ [ሀ]ደቀመዛሙርት እጁን በመጫን የተናገራቸው ቃላት—

፪ እናም በስማቸውም በመጥራት እንዲህ አላቸው፥ በብርቱ ፀሎት አብን በስሜ ጥሩት፤ እናም ይህንንም ካደረጋችሁ በኋላ [ሀ]እጃችሁን በምትጭኑበት ላይ መንፈስ ቅዱስን ለመስጠት [ለ]ስልጣን ይኖራችኋል፤ እናም በስሜም [ሐ]ትሰጡታላችሁ፣ ይህንንም ሐዋሪያቶቼ ያደርጉታልና።

፫ እንግዲህ ክርስቶስ በመጀመሪያም እራሱን ለእነርሱ ሲገልፅ እነዚህን ቃላት ተናግሯል፤ እናም ህዝቡም አላዳመጡም፤ ነገር ግን ደቀመዛሙርቱ አዳምጠውታል፤ እናም እጃቸውን [ሀ]በጫኑባቸው በሙሉ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው።

ምዕራፍ ፫

ሽማግሌዎች እጃቸውን በካህናት እናም በመምህራን ላይ በመጫን ሾሙአቸው። ፬፻፩–፬፻፳፩ ዓ.ም. ገደማ።

፩ የቤተክርስቲያኗ [ሀ]ሽማግሌዎች ተብለው የሚጠሩት ደቀመዛሙርት ካህናትን እና መምህራንን [ለ]የሚሾሙበት ስርዓት—

፪ ወደ አብ በክርስቶስ ስም ከፀለዩ በኋላ፣ እጃቸውን ጭነውባቸው እንዲህ አሉ፥

፫ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ካህን እንድትሆን (መምህር ከሆነ መምህር እንድትሆን)፣ ንስሃን እናም በኢየሱስ ክርስቶስ [ሀ]ለኃጢአታቸው ስርየትን በስሙ እስከመጨረሻው በእምነት በመፅናት እንደሚያገኙ እንድትሰብክ እሾምሃለሁ። አሜን።

፬ እናም በዚህ ስርዓት ለሰዎች በእግዚአብሔር [ሀ]ስጦታና ጥሪ መሰረት ካህናትን እናም መምህራንን [ለ]ይሾሙ ነበር፤ እናም በውስጣቸው ባለው በመንፈስ ቅዱስ [ሐ]ኃይልም ሾሙአቸው።

፩ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. ሞሮኒ፣ የሞርሞን ልጅ።
፪ ሀ ፩ ኔፊ ፲፪፥፳–፳፫።
ለ አልማ ፵፭፥፲፬።
፫ ሀ ማቴ. ፲፥፴፪–፴፫፤ ፫ ኔፊ ፳፱፥፭።
፪ ፩ ሀ ፫ ኔፊ ፲፫፥፳፭።
፪ ሀ ቅ.መ.መ. እጅን መጫን።
ለ ቅ.መ.መ. ሀይል።
ሐ ፫ ኔፊ ፲፰፥፴፯።
፫ ሀ የሐዋ. ፲፱፥፮።
፫ ፩ ሀ አልማ ፮፥፩።
ቅ.መ.መ. ሽማግሌ።
ለ ቅ.መ.መ. መሾም፣ ሹመት።
፫ ሀ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ስርየት።
፬ ሀ ቅ.መ.መ. ስጦታ።
ለ ት. እና ቃ. ፲፰፥፴፪፤ ፳፥፷።
ሐ ፩ ኔፊ ፲፫፥፴፯፤ ሞሮኒ ፮፥፱።

ምዕራፍ ፬

ሽማግሌዎች እና ካህናት የቅዱስ ቁርባንን ዳቦ እንዴት እንደሚባርኩት ተገልጿል። ፬፻–፬፻፳፩ ዓ.ም. ገደማ።

፩ [ሀ]ሽማግሌዎቻቸው እናም ካህናቶቻቸው የክርስቶስን ስጋና ደም ለቤተክርስቲያን በመባረክ የሚያስተላልፉት [ለ]ስርዓት፤ እናም በረከቱንም [ሐ]የሚያደርጉት እንደ ክርስቶስ ትዕዛዝ ነው፣ ስለዚህ ስርዓቱም ትክክል እንደሆነም እናውቃለን፤ እናም ሽማግሌው ወይም ካህኑ ይባርኩታል—

፪ እናም ከቤተክርስቲያኗ አባላትም ጋር ይንበረከካሉ፣ እናም በክርስቶስ ስምም እንዲህ ሲሉ ወደ አብ ይፀልያሉ፥

፫ አቤቱ ዘለዓለማዊ አባት እግዚአብሔር ሆይ፣ ይህንን [ሀ]ዳቦ ለሚቋደሱት ነፍሳት ሁሉ የልጅህን አካል [ለ]በማስታወስ እንዲበሉት እና፣ አቤቱ ዘለዓለማዊ አባት እግዚአብሔር ሆይ፣ እነርሱ [ሐ]የልጅህን ስም በላያቸው ላይ ለመውሰድ ፈቃደኞች መሆናቸውን፣ እና ሁልጊዜ እርሱን እንደሚያስታውሱና እርሱ የሰጣቸውን ትእዛዛት እንደሚጠብቁ ለአንተም ይመሰክሩ ዘንድ፣ በዚህም የእርሱ [መ]መንፈስ ሁልጊዜ እንዲኖራቸው ትባርከውና ትቀድሰው ዘንድ በልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንጠይቅሃለን። አሜን።

ምዕራፍ ፭

የቅዱስ ቁርባኑን ወይን የሚባረክበት ስርዓት እንደሚከተለው ተገልጿል። ፬፻፩–፬፻፳፩ ዓ.ም. ገደማ።

፩ ወይኑን የሚባረክበትም [ሀ]ስርዓት—እነሆ ዋንጫውን ወስደው እንዲህ ይላሉ፥

፪ አቤቱ ዘለዓለማዊ አባት እግዚአብሔር ሆይ፣ ይህንን [ሀ]ወይን የሚጠጡት ነፍሳት ሁሉ ለእነርሱ የፈሰሰውን የልጅህን ደም [ለ]በማስታወስ ያደርጉት ዘንድ፣ ሁልጊዜ እርሱን እንደሚያስታውሱ ለአንተም፣ አቤቱ ዘለዓለማዊ አባት እግዚአብሔር ሆይ፣ ይመሰክሩ ዘንድ፣ በዚህም የእርሱ መንፈስ እንዲኖራቸው፣ ትባርከውና ትቀድሰው ዘንድ በልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንጠይቅሃለን። አሜን።

ምዕራፍ ፮

ንሰሃ የገቡት ሰዎች ተጠመቁ እናም የቤተክርስቲያኗን ህብረት አገኙ—ንሰሃ የገቡ የቤተክርስቲያን አባላት ይቅርታን ተቀበሉ—ስብሰባዎች በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተከናውነዋል። ከ፬፻፩–፬፻፳፩ ዓ.ም. ገደማ።

፩ እናም አሁን [ሀ]ጥምቀትን በተመለከተ እናገራለሁ። እነሆ ሽማግሌዎች፣ ካህናት፣ እናም መምህራን ተጠምቀዋል፤ እናም ለእዚህም [ለ]ብቁ የሆኑ ትክክለኛ ፍሬ የሚያመጡ ካልሆኑ በስተቀር እነርሱ አይጠመቁም።

፪ [ሀ]በተሰበረ ልብ እናም በተዋረደ መንፈስ ካልመጡ እናም ለኃጢአታቸው በሙሉ በእውነት ንሰሃ እንደገቡ ለቤተክርስቲያኗ ካልመሰከሩ በስተቀር ወደ ጥምቀቱ ማንንም አልተቀበሉም።

፫ እናም የክርስቶስን ስም [ሀ]ካልለበሱ እናም እስከመጨረሻውም እርሱን ለማገልገል ካልወሰኑ በቀር ማንንም በጥምቀት አልተቀበሉም።

፬ እናም ከተጠመቁ እናም የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በላያቸው ላይ ከሰራ እናም [ሀ]ካነፃቸው

፬ ፩ሀ ቅ.መ.መ. ሽማግሌ።
ለ ፫ ኔፊ ፲፰፥፩–፯።
ሐ ት. እና ቃ. ፳፥፸፯–፸፱።
፫ሀ ቅ.መ.መ. ቅዱስ ቁርባን።
ለ ሉቃ. ፳፪፥፲፱፤
፩ ቆሮ. ፲፩፥፳፫–፳፬፤
፫ ኔፊ ፲፰፥፯።
ሐ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—የክርስቶስን ስም በራሳችን ላይ መውሰድ።
መ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
፭ ፩ሀ ፫ ኔፊ ፲፰፥፰–፲፩፤
ት. እና ቃ. ፳፥፸፰–፸፱።
፪ሀ ት. እና ቃ. ፳፯፥፪–፬።
ቅ.መ.መ. ቅዱስ ቁርባን።
ለ ሉቃ. ፳፪፥፲፱–፳፤
፩ ቆሮ. ፲፩፥፳፭።
፮ ፩ሀ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣ መጥመቅ።
ለ ቅ.መ.መ. ብቁ፣ ብቁነት።
፪ሀ ቅ.መ.መ. የተሰበረ ልብ።
፫ሀ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—የክርስቶስን ስም በራሳችን ላይ መውሰድ።
፬ሀ ቅ.መ.መ. ንጹህ፣ ንጹህነት።

በኋላ፣ ከክርስቶስ ቤተክርስቲያን ህዝቦች ጋር ተቆጥረዋል፤ እናም እነርሱን በትክክ ለኛው መንገድ ለማቆየት፣ የእምነታቸው ^ደራሲ እና ፈፃሚ በሆነው በክርስቶስ በጎ ሥራ ላይ ብቻ ^በመደገፍ ፀሎታቸውን ያለ ማቋረጥ እንዲሚቀጥሉ ^ለመጠበቅ፣ የእግ ዚአብሔርን መልካም ቃል በመመገብ ይታ ወሱ ዘንድ ^ስማቸው ተወስደዋል።

፭ እናም ^ለመፆም እናም ለመፀለይ፣ እናም እያንዳንዳቸው ለነፍሳቸው ደህን ነት እርስ በርሳቸው እንዲናገሩ ዘንድ ^ሁል ጊዜ ^በቤተክርስቲያን ይገኛሉ።

፮ እናም ጌታ ኢየሱስን ለማስታወስ ዳቦ ውን እና ወይኑን ለመካፈል፣ ሁልጊዜ በአ ንድነት ይሰበሰቡ ነበር።

፯ እናም በመካከላቸው ^ክፉ ነገር እንዳይ ኖርም በጥብቅ ይጠነቀቃሉ፤ በመካከላቸው ክፉ ነገር ሲያደርጉ የተገኙ፣ እናም በቤተ ክርስቲያኗ ^ሦስት ምስክሮች ^በሽማግሌ ዎች ፊት ከተወቀሱ፣ እናም ንሰሃም ካል ገቡ፣ እናም ^ካልተናዘዙ ስማቸው ^ይሰ ረዛል፣ እናም ከክርስቶስ ሰዎች ጋርም አይ ቆጠሩም።

፰ ነገር ግን በእውነተኛ ፍላጎት ንሰሃ ^ሁል ጊዜም ከገቡ፣ እናም ይቅርታን ከፈ ለጉ ^ይቅር ይባላሉ።

፱ እናም ስብሰባዎችም በቤተክርስቲያኗ በመንፈስ ስራዎች እናም ^በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ^ይመራል፤ የመንፈስ ቅዱስ ኃይ ልም እንዲሰብኩ፣ ወይም እንዲያስጠነ ቅቁ፣ ወይም እንዲፀልዩ፣ ወይም ወደጌታ እንዲማፀኑ ወይም እንዲዘምሩ ይመራቸ ዋል፣ እንዲሁም ይፈጸማል።

ምዕራፍ ፲

በጌታ እረፍት እንዲገቡ ሰዎች ተጋብዘ ዋል—በእውነተኛ ፍላጎት ፀልዩ—የክ ርስቶስ መንፈስ ሰዎች መጥፎውን ከጥሩ ለይተው እንዲያውቁ ያስችላቸዋል—ሰይ ጣን ሰዎች ክርስቶስን እንዲክዱ እናም መጥፎ እንዲሰሩ ይገፋፋቸዋል—ነቢያት ስለክርስቶስ መምጣት ተናግረዋል—በእ ምነት፣ ድንቅ ነገር ይሰራል፣ እናም መላ ዕክቶችም ያገለግላሉ—ሰዎች ዘለዓለማዊ ህይወትን ተስፋ ማድረግ እናም ከልግ ስናም ጋር ፅኑ መሆን አለባቸው። ፬ የ፬–፬ የ፳፯ ዓ.ም. ገደማ።

፩ እናም እንግዲህ እኔ ሞሮኒ፣ አባቴ ሞር ሞን ^ስለእምነት፤ ተስፋ እና ልግስና ከተ ናገራቸው ቃላት ጥቂቱን እፅፋለሁ፤ ለማ ምለኪያ በሰሩት ቦታም በምኩራብ ባስተ ማራቸው ጊዜ ለህዝቡ በዚህ አይነት ተና ግሮአልና።

፪ እናም እንግዲህ የተወደዳችሁ ወንድ ሞቼ እኔ ሞርሞን እናገራችኋለሁ፤ እናም በእግዚአብሔር አብ ፀጋ እናም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እናም በቅዱሱ ፈቃዱ፣ ^በተጠራሁበትም ሥጦታ ምክንያት በዚህ ጊዜ እንድናገራችሁ ተፈቅዶልኛል።

፫ ስለዚህ፣ የቤተክርስቲያኗ አባላት ለሆ ናችሁ፤ ሰላማዊ የክርስቶስ ተከታይ ለሆና ችሁ እናም ከዚህን ጊዜ ጀምሮ በሰማይ ከእ ርሱ ጋር ታርፉ ዘንድ፣ በጌታ ^በእረፍቱም ለመግባት እንድትችሉ በቂ ተስፋ ላገኛችሁ ይህን እናገራችኋለሁ።

፬ እናም እንግዲህ ወንድሞቼ፤ ከሰዎች

፩ ^ለ ዕብ. ፲፪ ፡ ፪።
^ሐ ፪ ኔፊ ፴፩ ፡ ፲፱፤
ት. እና ቃ. ፫ ፡ ፳።
^መ አልማ ፴፬ ፡ ፴፱፤
፫ ኔፊ ፲፰ ፡ ፲፭–፲፰።
^ሠ ት. እና ቃ. ፳ ፡ ፹፪።
፩ ^ሀ ቅ.መ.መ. ጾም፡ መጾም።
^ለ ፫ ኔፊ ፲፰ ፡ ፳፪፤
፬ ኔፊ ፩ ፡ ፲፪፤
ት. እና ቃ. ፹፰ ፡ ፫፯።
^ሐ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን።
፲ ^ሀ ት. እና ቃ. ፳ ፡ ፶፬።
^ለ ት. እና ቃ. ፶፪ ፡ ፹–፹፩።
ቅ.መ.መ. ምስክር።
^ሐ አልማ ፮ ፡ ፩።
ቅ.መ.መ. ሽማግሌ።
^መ ቅ.መ.መ. መናዘዝ።
^ሠ ዘፀአ. ፴፪ ፡ ፴፫፤
ት. እና ቃ. ፳ ፡ ፹፫።
ቅ.መ.መ. ውግዘት።
፲፩ ^ሀ ሞዛያ ፳፯ ፡ ፴–፴፩።
^ለ ቅ.መ.መ. ይቅርታ ማድረግ።
፲፪ ^ሀ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
^ለ ት. እና ቃ. ፳ ፡ ፶፭፤ ፶፯ ፡ ፪።
፲፫ ፩ ^ሀ ፩ ቆሮ. ፲፫፤
ኤተር ፲፪ ፡ ፫–፳፪፤ ፳፯–፴፯፤
ሞሮኒ ፲ ፡ ፲፱፤ ፲ ፡ ፳–፳፫።
፲፪ ^ሀ ቅ.መ.መ. ጥሪ፣
በእግዚአብሔር መጠራት፣
የተጠራበት።
፫ ^ሀ ቅ.መ.መ. እረፍት።

ልጆች ጋር ባላችሁ ሰላማዊ ᵐሂደት ምክን
ያት ስለእናንተ እንደዚህ እፈርዳለሁ።
፭ በሥራዎቻቸው ᵐታውቁአቸዋላችሁ
የሚለውንም የእግዚአብሔር ቃል አስታ
ውሳለሁ፤ ሥራዎቻቸው መልካም ከሆኑ
እነርሱም ደግሞ መልካም ናቸውና።
፮ እነሆም፣ እግዚአብሔርም ᵐክፉ የሆነ
ሰው መልካም የሆነን ለመስራት አይቻለ
ውም ብሏል፤ እርሱም ስጦታን ቢያቀርብ
እንዲሁም ወደ እግዚአብሔር ᵃቢፀልይ
ከእውነተኛ ፍላጎት ካልሆነ በቀር ምንም
አይጠቅመውም።
፯ እነሆም፣ ለእርሱም እንደፅድቅ አይ
ቆጠርለትም።
፰ እነሆም፣ ᵐክፉ የሆነ ሰው ስጦታ የሚ
ሰጥ ከሆነ፣ ᵃበመሰሰት ያደርጋል፤ ስለዚህ
ስጦታውን ለራሱ እንዳስቀረውም አይነት
ይቆጠርለታል፤ ስለዚህ በእግዚአብሔር
ፊት እንደክፉ ይቆጠራል።
፱ እናም በተመሳሳይ ደግሞ ሰው ᵐበእው
ነት ከልቡ በመፈለግ ካልፀለየ በመጥፎ ይቆ
ጠርለታል፤ አዎን፣ እናም ለእርሱ ምንም
አይጠቅመውም፣ ምክንያቱም እግዚአብ
ሔር እንደዚህ አይነቱን ማንም አይቀበል
ምና።
፲ ስለዚህ፣ መጥፎ የሆነ ሰው መልካም
የሆነውን ለመስራት አይቻለውምና፤ መል
ካም ስጦታም አይሰጥም።
፲፩ እነሆም፣ መራራ ᵐምንጭ መልካም
ውኃን ሊያፈልቅ አይቻለውም፤ ወይም
መልካም ምንጭም መራራን ውሃ ሊያፈ
ልቅ አይቻለውም፤ ስለዚህ፣ የዲያብሎስ
አገልጋይ የሆነ ሰውም ክርስቶስን ᵃለመከ
ተል አይችልም፤ እናም ክርስቶስን የሚ
ከተል ከሆነ የዲያብሎስ አገልጋይ ሊሆን
አይችልም።
፲፪ ስለዚህ፣ ᵐመልካም የሆኑ ነገሮች
በሙሉ ከእግዚአብሔር ይመጣሉ፤ እናም
ᵃመጥፎ የሆኑም ከዲያብሎስ ይመጣሉ፤
ዲያብሎስ የእግዚአብሔር ጠላት በመሆኑ፣
ያለማቋረጥ ከእርሱ ጋር ይዋጋል፣ እናም
ሰዎች ᵃኃጢያት እንዲሰሩ እናም ያለማ
ቋረጥ ክፉ የሆኑትን እንዲሰሩ ይጋብዛቸ
ዋል፣ እንዲሁም ይገፋፋቸዋል።
፲፫ ነገር ግን እነሆ፣ የእግዚአብሔር የሆነ
ያለማቋረጥ መልካምን እንዲሰሩ ᵐይጋብ
ዛል እናም ይገፋፋል፤ ስለዚህ፣ መልካምን
ለመስራት፣ እናም እግዚአብሔርን እንድ
ናፈቅር እናም እንድናገለግለው የሚጋብዝ
እናም ᵃየሚገፋፋ ማንኛውም ነገር ከእግዚ
አብሔር የሆነ ነው።
፲፬ ስለዚህ፣ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ፣
አድምጡ፣ ᵐክፉ የሆነው ከእግዚአብሔር
ነው በማለት፣ ወይንም መልካምና ከእግ
ዚአብሔር የሆነውን ከዲያብሎስ ነው በማ
ለት አትፍረዱ።
፲፭ እነሆም፣ ወንድሞቼ፣ ጥሩውን ከመ
ጥፎ ለይታችሁ ታውቁ ዘንድ ᵐእንድትፈ
ርዱ ተሰጥቷችኋል፤ እናም ፍፁም በሆነ
ዕውቀት ልታውቁ እንድትችሉ፣ ጥሩውን
ከመጥፎ የመፍረጃ መንገድ ጨለማን ከብ
ርሃን ለይቶ እንደሚያሳይ ያህል ግልፅ ነው።
፲፮ እነሆም፣ እያንዳንዱ ሰው መልካሙን
ከመጥፎው ለይቶ ᵐያውቅ ዘንድ ᵃየክርስ
ቶስ መንፈስ ተሰጥቶታል፤ ስለዚህ፣ እን
ዴት እንደምትፈርዱም መንገዱን አሳያች

፩ ᵐ ፩ ዮሐ. ፪፡ ፮፤
ት. እና ቃ. ፲፱፡ ፳፫።
፭ ᵐ ፫ ኔፊ ፲፰፡ ፲፭–፳።
፮ ᵐ ማቴ. ፯፡ ፲፭–፲፮።
ᵃ አልማ ፴፩፡ ፳፮።
ቅ.መ.መ. ጸሎት።
፰ ᵐ ምሳ. ፲፭፡ ፰።
ᵃ ት. እና ቃ. ፰፩፡ ፴፩።
፱ ᵐ ያዕ. ፩፡ ፯–፯፤ ፭፡ ፲፯፤
ሞሮኒ ፲፡ ፀ።
፲፩ ᵐ ያዕ. ፫፡ ፲፩–፲፪።
ᵃ ማቴ. ፯፡ ፳፩፤
፪ ኔፊ ፴፩፡ ፲–፲፫፤
ት. እና ቃ. ፶፯፡ ፪።
፲፪ ᵐ ያዕ. ፩፡ ፲፯፤
፩ ዮሐ. ፡ ፩–፪፤
ኤተር ፬፡ ፲፪።
ᵃ አልማ ፭፡ ፴፱–፵፪።
ሐ ሔለ. ፮፡ ፴።
ቅ.መ.መ. ኃጢያት።
፲፫ ᵐ ፪ ኔፊ ፴፫፡ ፬፤
ኤተር ፰፡ ፳፯።
ᵃ ቅ.መ.መ. መነሳሻ፣
መነሳሳት።
፲፬ ᵐ ኢሳ. ፭፡ ፳፣
፪ ኔፊ ፲፭፡ ፳።
፲፭ ᵐ ቅ.መ.መ. የመለየት ስጦታ።
፲፮ ᵐ ዘፍጥ. ፫፡ ፭፤
፪ ኔፊ ፪፡ ፭፣ ፲፰፡ ፳፯፤
ሞዛያ ፲፮፡ ፫፤
አልማ ፳፱፡ ፭፤
ሔለ. ፲፡ ፴፩።
ᵃ ቅ.መ.መ. ህሊና፣
ብርሀን፣ የክርስቶስ ብርሀን።

ኋለሁ፤ መልካም ነገሮችን ለማድረግ የሚ
ጋብዝ እናም በክርስቶስ ሰዎች እንዲያምኑ
ለማሳመን የሚያደርግ የተላከው በክርስቶስ
ኃይል እና ስጦታ አማካኝነት ነው፤ ስለዚህ
ይህ ከእግዚአብሔር መሆኑን ፍፁም በሆነ
ዕውቀት ታውቃላችሁ።

፲፯ ነገር ግን ሰዎች ᵐመጥፎ እንዲሰሩ፤
እናም በክርስቶስ እንዳያምኑ፣ እናም እን
ዲክዱት፣ እናም እግዚአብሔርን እንዳ
ያገለግሉ የሚያሳምናቸው፣ ይህም ከዲ
ያብሎስ መሆኑን ፍፁም በሆነ ዕውቀት
ልታውቁ ትችላላችሁ፤ ምክንያቱም በዚህ
ሁኔታ ዲያብሎስ ይሰራልና፣ እርሱም
ማንንም ሰው መልካም እንዲሰራ አይገ
ፋፋም፣ አንድም አይገፋፋም፤ መላዕክ
ቶቹም ቢሆኑ ይህንን አያደርጉም፤ እራሳ
ቸውን የእርሱ ያደረጉትም ቢሆኑ እንዲህ
አያደርጉም።

፲፰ እናም እንግዲህ፣ ወንድሞቼ፣ በእር
ግጥ የምትፈርዱበትን ብርሃን ማወቃችሁን
በመመልከት፣ ብርሃኑም ᵐየክርስቶስ ብር
ሃን ነው፣ በስህተት ᶠእንደማትፈርዱ እርግ
ጠኞች ሁኑ፤ ምክንያቱም በምትፈርዱበት
ፍርድ ደግሞ ይፈረድባችኋልና።

፲፱ ስለዚህ፣ ወንድሞቼ ᵐበክርስቶስ ብር
ሃን መልካሙን ከመጥፎው ታውቁ ዘንድ
በትጋት እንድትፈልጉ እለምናችኋለሁ፤
እናም መልካም የሆኑትን ሁሉ የምትይዙ
ከሆነ፣ እናም ካልኮነናችሁት፣ በእርግጥ
እናንተ የክርስቶስ ᶠልጆች ትሆናላችሁ።

፳ እናም አሁን፣ ወንድሞቼ፣ እንዴትስ
መልካም የሆኑትን ሁሉ ለመያዝ ይቻላች
ኋል?

፳፩ እናም አሁን እናገራለሁ ስላልኩት
እምነት በተመለከተ እናገራለሁ፤ እናም
መልካም የሆኑትን ነገሮች የምትይዙበትን
መንገዱን እነግራችኋለሁ።

፳፪ እነሆም፣ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር
ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ᵐበማወቁ፣
እነሆ፣ እርሱም የሰው ልጆችን እንዲያገ
ለግሉ፣ የክርስቶስን መምጣት በተመለከተ
እንዲገልጡ ᶠመላዕክትን ልኳል፤ እናም
በክርስቶስ መልካም ነገር በሙሉ ይመጣል።

፳፫ እናም እግዚአብሔር ደግሞ በአንደ
በቱ ለነቢያት ክርስቶስ እንደሚመጣ ተና
ግሯቸዋል።

፳፬ እናም እነሆ፣ መልካም ነገሮችን ለሰው
ልጆች የገለጠበት የተለያዩ መንገዶች ነበ
ሩት፤ እናም መልካም የሆኑ ነገሮች በሙሉ
የሚመጡት ከክርስቶስ ነው፤ አለበለዚያ
ሰዎች ᵐየወደቁ ናቸው፣ እናም መልካም
ነገርም ወደ እነርሱ ሊመጣ አይቻለውም።

፳፭ ስለዚህ፣ ᵐበመላዕክት አገልግሎት
አማካይነት እናም ከእግዚአብሔርም አን
ደበት በሚወጡት በእያንዳንዱ ቃላት፣
ሰዎች በክርስቶስ ታማኝ መሆን ጀምረዋል፤
እናም በእምነታቸውም መልካም የሆኑትን
ነገሮች በሙሉ ለማግኘት ችለዋል፤ እናም
ይህም የሚሆነው ክርስቶስ እስከሚመጣ
ድረስ ነው።

፳፮ እናም እርሱም ከመጣ በኋላ ሰዎች
ደግሞ በስሙ በማመናቸው ድነዋል፤ እናም
በእምነታቸው የእግዚአብሔር ልጆች ሆነ
ዋል። እናም ክርስቶስ በእርግጥም ህያው
እንደሆነ ለአባቶቻችን እነዚህን ቃላት እን
ዲህ ሲል ተናግሯል፥ በስሜ ትክክል የሆነ
ውን ᵐማንኛውንም ነገር በእምነት እናገኛለን
በማለት አብን ከጠየቃችሁት፤ እነሆ ለእና
ንተ ይሰጣችኋል።

፳፯ ስለሆነም፣ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ፣

፲፯ ᵐ ቅ.መ.መ. ኃጢያት።
፲፰ ᵐ ሞዛያ ፲፮፡ ፱፤
ት. እና ቃ. ፶፡ ፳፩፤
፹፰፡ ፮–፲፫።
ቅ.መ.መ. ብርሀን፣ የክርስቶስ
ብርሀን።
ᶠ ጆ.ስ.ት. ማቴ. ፯፡ ፩–፪
(ተጨማሪ)፤
ሉቃ. ፮፡ ፴፯፤
ዮሐ. ፯፡ ፳፬።
፲፱ ᵐ ት. እና ቃ. ፹፬፡ ፣ ፹፭–፹፮።
ᶠ ሞዛያ ፲፭፡ ፲–፲፪፤ ፳፯፡ ፳፭።
ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር
ወንድ እና ሴት ልጆች።
፳፪ ᵐ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣
አምላክ።
ᶠ ሙሴ ፭፡ ፻፳።
ቅ.መ.መ. መላእክት።
፳፬ ᵐ ፪ ኔፊ ፪፡ ፭።
፳፭ ᵐ አልማ ፲፪፡ ፳፰–፴።
፳፮ ᵐ ፫ ኔፊ ፲፰፡ ፳።
ቅ.መ.መ. ጸሎት።

ክርስቶስ ወደ ሰማይ በማረጉ እናም አብን በሰዎች ልጆች ላይ ያለውን ምህረት ᵐለመ ጠየቅ በእግዚአብሔር ቀኝ እጅ በኩል በመ ቀመጡ ᵃተአምራት ቆመዋልን?

፳፯ እርሱም የህጉን ፍፃሜ አሟልቶ ታል፣ እናም በእርሱ እምነት ያላቸውን በሙሉ የእርሱ አድርጓል፤ እናም በእርሱ እምነት ያላቸው መልካሙን ነገር በሙሉ ᵐይይዛሉ፤ ስለሆነም እርሱም ለሰው ልጆች ጉዳይ ᵃጠበቃ ይሆናል፤ እናም ለዘለዓለም በሰማያት ይኖራል።

፳፰ እናም ይህንን በማድረጉ የተወደዳ ችሁ ወንድሞቼ፣ ተአምራት ቆመዋልን? እነሆ አልቆሙም እላችኋለሁ፤ መላዕክቶ ችም ቢሆኑ የሰው ልጆችን ማገልገላቸውን አላቆሙም።

፳፱ እነሆም፣ እነርሱም በትእዛዙ ቃል መሰረት ለማገልገል፤ ጠንካራ እምነት እና በመለኮታዊነት አስተያየት በሙሉ ፅኑ አዕ ምሮ ላላቸው እራሳቸውን ለማሳየት ለእርሱ የተገዙ ናቸው።

፴፩ እናም በአገልግሎታቸውም ኃላፊነ ታቸው ሰዎችን ወደ ንሰሃ መጥራት፣ እናም አብም ለሰው ልጆች የገባውን የቃል ኪዳን ስራ ለማከናወን እና ለመፈፀም፣ በጌታ ለተ መረጡት አገልጋዮችም ምስክርነታቸውን ይሰጡ ዘንድ የክርስቶስን ቃል ለመናገር በሰው ልጆች መካከል መንገዱን ለማዘጋ ጀት ነው።

፴፪ እናም ይህንን በማድረግ፣ የተቀ ሩት ሰዎች በክርስቶስ ᵐእምነት እንዲኖ ራቸው፣ ባለው ሀይል መሰረትም መንፈስ ቅዱስ በልባቸው ስፍራ እንዲነኖረው ጌታ አምላክ መንገዱን ያዘጋጃል፤ እናም በዚ ህም ስርዓት አብ ለሰው ልጆች የገባውን ቃል ኪዳን ይፈፅማል።

፴፫ እናም ክርስቶስ እንዲህ ብሏል፥ በእኔ እምነት ᵐካላችሁ እኔ ᵃአስፈላጊ የሆነውን ማንኛውንም ነገር ለመስራት ኃይል ይኖ ራችኋል።

፴፬ እናም እንዲህ ብሏል፥ እስከ ምድር ዳርቻ ያላችሁ ሁሉ ᵐንሰሃ ግቡ፣ እናም ወደ እኔ ኑ፣ እናም በስሜ ተጠመቁ፣ እናም ትድኑም ዘንድ በእኔ እምነት ይኑራችሁ።

፴፭ እናም እንግዲህ፣ የተወደዳችሁ ወን ድሞቼ፣ ሁኔታው እንዲህ ከሆነ የተናገርኳ ችሁ እነዚህ ነገሮች እውነት ከሆኑ፣ እናም እውነት መሆናቸውንም እግዚአብሔር ᵐበኃይል እናም በታላቅ ክብር በመጨረ ሻው ᵃቀን ካሳያችሁ፣ እናም እውነት ከሆ ኑስ የተአምራቱ ቀን ቆሟልን?

፴፮ መላዕክትስ ለሰው ልጆች መታየታ ቸውን አቁመዋልን? ወይስ እግዚአብሔርስ የመንፈስ ቅዱስን ኃይሉን ከእነርሱ ᵐእር ቋልን? ወይንስ እስከመጨረሻው፣ ወይ ንም መሬት እስካለች፣ ወይም በምድር ላይ ለመዳን አንድ ሰው እስካለ ድረስ ይህን ያደ ርጋልን?

፴፯ እነሆ አያስቀርም እላችኋለሁ፤ ምክ ንያቱም ᵐተአምራት የሚከናወኑት በእምነት ነው፤ እናም መላዕክቶችም ለሰዎች የሚ ታዩት እና የሚያገለግሉት በእምነት ነው፤ ስለሆነም፣ እነዚህ ነገሮች ካቆሙ ለሰው ልጆች ወዮላቸው፤ ምክንያቱም እነዚህ ነገሮች የሚቆሙት ᵃባለማመናቸው ነው፣ እናም ሁሉም ከንቱ ይሆናል።

፴፰ እንደ ክርስቶስ ቃል በእርሱ እምነት ከሌላቸው ማንም ሰው ለመዳን አይችልም፤ ስለሆነም፣ እነዚህ ነገሮች ከቆሙ፣ እምነ ትም ደግሞ ይቆማል፤ እናም የሰዎች ሁኔታ አሰቃቂ ይሆናል፣ ምክንያቱም ቤዛነት እን ዳልተፈፀመ ሆነው ይቆያሉና።

፳፯ ሀ ኢሳ. ፶፫ ፡ ፲፪፤
ሞዛያ ፲፬ ፡ ፲፪።
ለ ቅ.መ.መ. ተአምራት።
፳፰ ሀ ሮሜ ፲፪ ፡ ፱፤
ት.እና ቃ. ፻፳ ፡ ፲፩።
ለ ፩ ዮሐ. ፪ ፡ ፩፤
፪ ኔፊ ፪ ፡ ፱።

ቅ.መ.መ. አማላጅ።
፳፱ ሀ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
፴፫ ሀ ማቴ. ፲፯ ፡ ፳።
ለ ት.እና ቃ. ፲፫ ፡ ፳፬–፳፭።
፴፬ ሀ ፫ ኔፊ ፳፯ ፡ ፳፤
ኤተር ፬ ፡ ፲፳።
፴፭ ሀ ፪ ኔፊ ፴፫ ፡ ፲፩።

ለ ት.እና ቃ. ፴፭ ፡ ፳።
፴፯ ሀ ሞሮኒ ፲ ፡ ፬–፭፣ ፯፣ ፲፱።
፴፯ ሀ ማቴ. ፲፫ ፡ ፶፳፤
ሞር. ፱ ፡ ፳፣
ኤተር ፲፪ ፡ ፲፪–፲፳።
ለ ሞሮኒ ፲ ፡ ፲፱–፳፬።

፴፱ ነገር ግን እነሆ፣ የተወደዳችሁ ወንድ ሞቼ፤ ስለእናንተ የተሻሉትን ነገሮች እፈር ዳለሁ፤ ምክንያቱም እናንተ የዋህ በመሆና ችሁ በክርስቶስ እምነት እንዳላችሁ እፈር ዳለሁ፤ ምክንያቱም በእርሱ እምነት ከሌ ላችሁ ከቤተክርስቲያኑ ሰዎች ጋር ለመቆ ጠር [ሀ]ብቁ አትሆኑምና።

፴ እናም የተወደዳችሁ ወንድሞቼ በድ ጋሚ [ለ]ተስፋን በተመለከተ እናገራችኋለሁ። ተስፋ ከሌላችሁ እምነትን እንዴት ለማግ ኘት ይቻላችኋል?

፴፩ እናም [ሐ]ተስፋ የምታደርጉበት ምንድ ነው? እነሆ በክርስቶስ የኃጢያት ክፍያ እናም በትንሳኤው ኃይል [መ]ለዘለዓለም ህይወት እን ዲኖራችሁ [ሠ]ተስፋ ይኑራችሁ እላችኋለሁ፤ እናም ይህም በእርሱ ባላችሁ እምነት ለእ ናንተ በገባላችሁ ቃል ኪዳን መሰረት ነው።

፴፪ ስለሆነም፣ አንድ ሰው [ረ]እምነት ካለው ተስፋ ሊኖረው [ሰ]ይገባል፤ ያለ እምነት ምንም ዓይነት ተስፋ ሊኖር አይችልምና።

፴፫ እናም በድጋሚ፣ እነሆ እንዲህ እላ ችኋለሁ፣ [ሸ]የዋህ እና በልቡ የሚራራ ካል ሆነ በስተቀር እምነት እና ተስፋ ሊኖረው አይችልም።

፴፬ ከሆነ ግን [ቀ]እምነቱ እና ተስፋው ከንቱ ነው፤ ምክንያቱም በልቡ የሚራራ እናም የዋህ ካልሆነ በጌታ ፊት ተቀባይነት አይ ኖረውምና፤ እናም ሰው የዋህ እናም በልቡ የሚራራ፣ እናም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ብሎ [በ]የሚመሰክር ከሆነ እርሱ ልግስና ሊኖረው ይገባዋል፤ ልግስና ግን ከሌለው እርሱ ከንቱ ነውና፤ ስለሆነም ልግስና ሊኖረው ይገባል።

፴፭ እናም [ተ]ልግስና ትታገሳለች፣ እናም ደግ ናት፣ እናም [ቸ]አትቀናም፣ እናም በኩ ራት አትወጠርም፣ የራሷን አትፈልግም፤ በቀላሉ አትቆጣም፣ ክፉ አታስብም፣ እናም በመጥፎ ስራ አትደሰትም፣ ነገር ግን በእው ነት ትደሰታለች፣ ሁሉንም ነገሮች ትታገሳ ለች፣ በሁሉም ነገሮች ታምናለች ሁሉንም ነገሮች ተስፋ ታደርጋለች፣ በሁሉም ነገ ሮች ትፀናለች።

፴፮ ስለዚህም፣ የተወደዳችሁ ወንድ ሞቼ፣ ልግስና ከሌላችሁ ከንቱዎች ናችሁ፣ ልግስና አትወድቅምና። ስለሆነም ከሁሉም በላይ ታላቅ የሆነችውን ልግስናን ያዙ፤ ሁሉም ነገሮች መውደቅ አለባቸውና—

፴፯ ነገር ግን [ተ]ልግስና ንፁህ የክርስቶስ [ፍ]ፍቅር ናት፣ እናም እስከዘለዓለም ትፀና ለች፤ እናም በመጨረሻው ቀንም እርሷን የያዘ መልካም ይሆንለታል።

፴፰ ስለሆነም የተወደዳችሁ ወንድሞቼ፣ በልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ [ተ]ከ ታዮች ሁሉ ላይ በሚያፈሰው በዚህ ፍቅር ትሞሉ ዘንድ፣ የእግዚአብሔር ልጆች ትሆኑ ዘንድ፣ እርሱ እንደሆነ እናየዋለንና፣ እርሱ በሚመጣበትም ጊዜ እንደ እርሱ [ሀ]እንሆን ዘንድ፣ ይህም ተስፋ ይኖረን ዘንድ፣ ልክ እርሱ ንጹህ እንደሆነ እኛም [ለ]ንጹህ እን ሆን ዘንድ በኃይል በሙሉ ልባችሁ ሀይል ወደ አብ [መ]ፀልዩ። አሜን።

ምዕራፍ ፰

ህጻናትን ማጥመቅ የከፋ ርኩሰት ነው—ህፃናት በክርስቶስ የኃጢያት ክፍያ አማ

፴፱ [ሀ] ቅ.መ.መ. ብቁ፣ ብቁነት።
፴ [ለ] ኤተር ፲፪፡፬፡ ቅ.መ.መ. ተስፋ።
፴፩ [ሐ] ት. እና ቃ. ፪፴፰፡ ፲፩፡
[መ] ቅ.መ.መ. የዘለዓለም ህይወት።
[ሠ] ቲቶ ፩፡ ፪፤ ያዕቆ. ፩፡ ፭፤ አልማ ፳፭፡ ፲፯፤ ሞሮኒ ፱፡ ፳፭፡
፴፪ [ረ] ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን፡
[ሰ] ሞሮኒ ፲፡ ፳፡
፴፫ [ሸ] ቅ.መ.መ. ገር፣ ገርነት፡
፴፬ [ቀ] አልማ ፯፡ ፳፬፤ ኤተር ፲፪፡ ፳፰–፴፡
[በ] ሉቃ. ፲፪፡ ፳–፱፡ ቅ.መ.መ. መናዘዝ፤ ምስክርነት፡
፴፭ [ተ] ፩ ቆሮ. ፲፫፡
[ቸ] ቅ.መ.መ. ቅናት፡
፴፮ [ኀ] ፪ ኔፊ ፳፯፡ ፴፡
ቅ.መ.መ. ልግስና፡
[ነ] ኢ.ያ. ፳፪፡ ፭፡ ቅ.መ.መ. ፍቅር፡
፴፯ [ኘ] ቅ.መ.መ. ታዛዥነት፣ ታዛዥ፣ መታዘዝ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ—የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ፡
[አ] ፩ ዮሐ. ፫፡ ፩–፫፤ ፫ ኔፊ ፳፯፡ ፳፯፡
[ከ] ፫ ኔፊ ፲፱፡ ፳፯–፳፱፡ ቅ.መ.መ. ንጹህ፣ ንጹህነት፡
[መ] ቅ.መ.መ. ጸሎት፡

ካይነት ህያው ናቸው—እምነት፣ ንሰሃ፣ የዋህነት እና የልብ ርህራሄ፣ መንፈስ ቅዱስን መቀበል፣ እና እስከ መጨረሻው ፅኑ መሆን ወደ ደህንነት ይመራል። ፬፻፩–፬፻፳፭ ዓ.ም. ገደማ።

፩ ᵐአባቴ ሞርሞን ለእኔ ለሞሮኒ የፃፈልኝ ደብዳቤ፣ እናም የተፃፈልኝ ወዲያው ለአገልግሎት ከተጠራሁ በኋላ ነበር። እናም በዚህም ሁኔታ እንዲህ ሲል ነበር የፃፈልኝ፥

፪ የተወደድክ ልጄ ሞሮኒ፣ ጌታህ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለአንተ ስለሚያስብልህ እናም ለአገልግሎት እናም ለቅዱሱ ስራው ስለ ጠራህ እጅግ ተደስቻለሁ።

፫ እናም በቅዱሱ ልጁ በኢየሱስ ስም ወደ እግዚአብሔር አብ ያለማቋረጥ በመፀለይ፣ እርሱም ወደር በሌለው ᵐቸርነቱ እንዲሁም ᵃፀጋው እስከመጨረሻው በእምነት የፀናህ እንድትሆን ይጠብቅህ ዘንድ፣ ሁል ጊዜ በፀሎቴ ስለአንተ አስባለሁ።

፬ እናም እንግዲህ፣ ልጄ እጅግ ያሳዘነኝን ነገር በተመለከተ እነግርሃለሁ፤ በመካከላ ችሁ ᵐክርክር በመነሳቱ እኔን አሳዝኖኛል።

፭ እውነቱን እንደተረዳሁት ከሆነ፣ የህጻ ናትን ጥምቀት በሚመለከት በመካከላችሁ ክርክር ነበር።

፮ እናም እንግዲህ፣ ልጄ ይህ ታላቅ ስህ ተትም ከመካከላችሁ እንዲወገድ ተግተህ እንድትሰራ እፈልጋለሁ፤ ለዚህ ስልም ይህንን ደብዳቤ ፃፍኩልህ።

፯ ስለእነዚህን ነገሮች ካንተ ካወቅሁኝ በኋላ ሁኔታውን በሚመለከት ጌታን ወዲ ያው ጠየቅኩኝ። እናም የጌታ ᵐቃልም በመ ንፈስ ቅዱስ ኃይል እንዲህ ሲል መጣልኝ፥

፰ የአዳኝህን፣ የጌታህን እናም የአምላክ ህን የክርስቶስን ቃል አድምጥ። እነሆ፣ ወደ ዓለም የመጣሁት ፃድቃንን ሳይሆን ኃጢአ ተኞችን ንሰሃ እንዲገቡ ልጠራ ነው፤ ሕመ ምተኞች እንጂ ᵐብርቱዎች ባለ መድኃኒት አያስፈልጋቸውም፤ ስለሆነም፣ ᵃህፃናት ᵐፍፁማን ናቸው፤ ᵐኃጢያትንም ለመ ፈፀም አይችሉምና፤ ስለሆነም፣ ᵐየአዳም እርግማን ከእነርሱ በእኔ ተወስዷል፤ በእነ ርሱ ላይ ምንም ኃይል የለውም፤ ᶜየግርዘት ህግም በእኔ ተሽሯል።

፱ እናም በዚህ ሁኔታ ነው መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ቃል የገለጠልኝ፤ ስለሆ ነም፣ የተወደድክ ልጄ፣ ህፃናትን ማጥመ ቅህ በእግዚአብሔር ፊት ከባድ ፈዝ መሆ ኑን አውቃለሁ።

፲ እነሆ ይህንን ነገር እንድታስተምር እልሃለሁ—ንስሀ መግባትን እና ጥምቀትን ᵐተጠያቂ ለሆኑት እና ኃጢያትን ለሚፈ ጽሙት፤ አዎን፣ ወላጆች ንሰሃ መግባት እናም መጠመቅ እንዳለባቸው፣ እናም እንደ ᵃህፃናቱ ልጆቻቸው እራሳቸውን የዋህ እን ዲያደርጉ አስተምራቸው፣ እናም ሁሉም ከህፃናት ከልጆቻቸው ጋር ይድናሉ።

፲፩ እናም ᵐህፃናት ልጆቻቸው ጥምቀትም ሆነ ንሰሃ አያስፈልጋቸውም። እነሆ ለንሰሃ መጠመቅ ትዕዛዙን ለመፈፀም እናም ለኃ ጢያት ᵃስርየት ነው።

፲፪ ነገር ግን ᵐህፃናት ልጆች በክርስቶስ ከዓለም መፈጠር ጀምሮም ህያው ናቸው፤ ይህ ባይሆን ኖሮ፣ እግዚአብሔር ፍትህ የሌ ለው እናም ደግሞ የሚለወጥ አምላክ እናም ለሰዎች ᵃየሚያደላ ነው፤ ምን ያህል ህፃ ናትስ ጥምቀትን ሳያገኙ ሞተዋልና!

፲ ᴱ ᵃ ቃላት ፩፡ ፩።
ᴮ ᵃ ሞዛያ ፩፡ ፲፩።
ᶜ ᵃ ቅ.መ.መ. ጸጋ።
ᴰ ᵃ ᴮ ኔፊ ፲፩፡ ፳፪፣ ፳፫፣ ፲፳፡ ፴፬።
ᴱ ᵃ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ቃል።
ᶠ ᵃ ማር. ፪፡ ፣ ፲፯።
ᵃ ማር. ፣ ፡ ፣ ፲ᴮ–፲፯።
ᵇ ሞዛያ ᴮ፡ ፲፯፣ ፡ ት. እና ቃ. ᶜ፲፩፡ ፯።
ᵐ ቅ.መ.መ. ኃጢያት።
ᵐ ᴱ ኔፊ ᴱ፡ ፳ᴱ–፳ᴱ።
ቅ.መ.መ. የአዳም እና የሔዋን ውድቀት።
ᶜ ዘፍጥ. ፣ ፡ ፣ ᴮ–፲፩።
ቅ.መ.መ. መግረዝ።
ᴰ ᵃ ቅ.መ.መ. መልስ መስጠት፣ ሂሳብ፣ ተጠያቂነት፣ ሀላፊነት።
ᵃ ቅ.መ.መ. ልጅ፣ ልጆች፣ ትሁት፣ ትሕትና።
ᴱ ᵃ ቅ.መ.መ. ልጅ፣ ልጆች፣ ጥምቀት፣ መጥመቅ—ለመጠመቅ ብቁነት።
ᵃ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ስርየት።
ᴮ ᵃ ት. እና ቃ. ᴮ፲ᴮ፡ ᴮ᳀ᴮ–᳀ᴮ፣ ᴮ᳀ᴮ፡ ᴮ᳀ᴮ።
ᵃ ኤፌ. ᴮ፡ ᴮ፣ ᴮ ᴮ ኔፊ ᴮᴮ፡ ᴮ᳀ᴮ፣ ᴮ᳀ᴮ፡ ᴮ᳀ᴮ።

፲፫ ስለዚህ፣ ህፃናት ያለጥምቀት መዳን ባይቻላቸው ኖሮ እነዚህም መጨረሻ ወደ ሌለው ገሃነም ይሄዱ ነበር።

፲፬ እነሆ እንዲህ እልሀለሁ፤ ህፃናት መጠመቅ እንዳለባቸው የሚገምት እርሱ በመራራው መርዝ እናም በክፋት ሰንሰለት ውስጥ ነው፤ ምክንያቱም እርሱ [a]እምነት፣ ተስፋም ሆነ ልግስና የለውምና፣ ስለዚህ፣ ይህንን እያሰበ ከሞተም፣ እርሱ ወደ ሲኦል መውረድ አለበት።

፲፭ እግዚአብሔር በጥምቀት አንድን ልጅ ያድናል፤ እናም ያልተጠመቁት ሌሎቹ ግን ይጠፋሉ ብሎ ማሰብ የከፋ ኃጢያት ነው።

፲፮ በዚህ ሁኔታ የጌታን መንገድ ለሚበክሉት ወዮላቸው፤ ምክንያቱም እነርሱ ንሰሃ ካልገቡ ይጠፋሉና። እነሆ፣ ከእግዚአብሔር [b]ስልጣን ስለተሰጠኝ በድፍረት እና ገራለሁ፤ እናም ሰው ለማድረግ የሚችለውን አልፈራም፤ ምክንያቱም ፍፁም የሆነ [c]ፍቅር ፍርሃትን ሁሉ [d]አውጥቶ ይጥላልና።

፲፯ እናም እኔ ዘለዓለማዊ ፍቅር በሆነው [e]ልግስና ተሞልቻለሁ፤ ስለሆነም፣ ህፃናት ሁሉ ለእኔ የሚመሳሰሉ ናቸው፤ ስለሆነም፣ [f]ህፃናትን ፍፁም በሆነ ፍቅር እወዳቸዋለሁ፤ እናም ሁሉም ተመሳሳይ ናቸው እናም ከደህንነቱም ተካፋዮች ናቸው።

፲፰ እግዚአብሔር የማያዳላ እናም [g]የማይለወጥ አምላክ እንደሆነ አውቃለሁ፤ ነገር ግን እርሱ ከዘለዓለም እስከዘለዓለም [h]በሙሉ አይለወጥም።

፲፱ [i]ህፃናት ንሰሃ ለመግባት አይችሉም፤ ስለሆነም፣ ለእነርሱ ንፁህ የሆነውን የእግዚአብሔርን ምህረት መካድ የከፋ ኃጢያት ነው፤ ምክንያቱም [j]በምህረቱ ሁሉም ህያው ሆነዋልና።

፳ እናም ህፃናት መጠመቅ አለባቸው የሚል የክርስቶስን [k]የኃጢያት ክፍያ የካደ ነው፣ እናም የእርሱን የኃጢያት ክፍያ እናም የቤዛነቱን ኃይል እንደምንም ንቀ ውታል።

፳፩ እነርሱም በሞት፣ [l]በሲኦል፣ እናም [m]መጨረሻ በሌለው ቅጣት አደጋ ላይ በመሆናቸው ወዮላቸው። በድፍረት እናገራለሁ፤ እግዚአብሔርም አዞኛል። እነርሱን ስሙ እናም አድምጡ፣ አለበለዚያ በክርስቶስ [n]የፍርድ ወንበር ፊት በእናንተ ላይ ለምስክር ይቆማሉና።

፳፪ እነሆ ህፃናት በሙሉ፣ እናም ደግሞ ህጉ የሌላቸው ሁሉ በክርስቶስ [o]ህያው ናቸውና። ምክንያቱም [p]የቤዛነት ኃይል [q]ህጉ ለሌላቸው ሁሉ ይመጣልና፤ ስለሆነም ያለ ተኮነነ ወይንም ኩነኔ የሌለበት ንሰሃ ለመግባት አይችልም፤ እናም ለእንደዚህ አይነቱ ሰው ጥምቀት ምንም ጥቅም የለውም—

፳፫ ነገር ግን ይህ በእግዚአብሔር ፊት መሳለቅ፣ የክርስቶስን ምህረት እናም የመንፈስ ቅዱሱን ኃይል መካድ፣ እናም [r]በሞተ ስራ ላይ ተስፋ ማድረግ ነው።

፳፬ እነሆ ልጄ ይህ ነገር መሆን የለበትም፤ ምክንያቱም [s]ንሰሃ የሚያስፈልገው በኩነኔ እናም በተጣሰው ህግ እርግማን ሥር ላሉት ነውና።

፳፭ እናም [t]የንሰሃ የመጀመሪያው ፍሬ [u]ጥምቀት ነው፤ እናም ጥምቀት የሚመ

፲፬ *ሀ* ፩ ቆሮ. ፲፫፣ ኤተር ፲፪፡፮፣ ሞሮኒ ፯፡፳፩–፳፳፣ ፲፡፳–፳፫።
፲፭ *ሀ* ቅ.መ.መ. ስልጣን።
ለ ቅ.መ.መ. ፍቅር።
ሐ ፩ ዮሐ. ፪፡፲፰።
፲፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. ልግስና።
ለ ሞዛያ ፫፡፲፯–፲፱።
፲፰ *ሀ* አልማ ፯፡፳፣ ሞር. ፱፡፱።
ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ።
ለ ሞሮኒ ፯፡፳፪።
፲፱ *ሀ* ሉቃ. ፲፰፡፲–፲፯።
ለ ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።
፳ *ሀ* ቅ.መ.መ. የቤዛነት ዕቅድ፣ የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ።
፳፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. ሲያል።
ለ ያዕቆ. ፭፡፲፣ ሞዛያ ፳፡፲፣ ት. እና ቃ. ፲፱፡፲–፲፪።
ሐ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—ዳኛ።
፳፪ *ሀ* ቅ.መ.መ. ደህንነት—የልጆች ደህንነት።
ለ ቅ.መ.መ. ቤዛ፣ ማዳን፣ ቤዛነት።
ሐ የሐዋ. ፲፯፡፴፣ ት. እና ቃ. ፫፯፡፫–፫፪።
፳፫ *ሀ* ት. እና ቃ. ፳፪፡፪።
፳፬ *ሀ* ቅ.መ.መ. መጸጸት፣ ንስሀ መግባት።
፳፭ *ሀ* ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣ መጥመቅ—ለመጠመቅ ብቁነት።
ለ ሙሴ ፮፡፶፱–፷።

ጣው በእምነት ትዕዛዙን በመፈፀም ነው፤ እናም ትዕዛዙን መፈፀም የኃጢያት ሐስር የትን ያመጣል፤

፳፪ እናም የኃጢያት ስርየት ᵐየዋህነትን፣ እና የልብ ርህራሄን ያመጣል፤ እናም የዋህ ነት እናም የልብ ርህራሄ ᵃበመንፈስ ቅዱስ መጎብኘትን ያመጣል፤ ይህም ᵇአፅናኝ ᶜበተስፋ እናም ᶜበፍፁም ፍቅር ይሞ ላል፣ ይህም ፍቅር ᵈቅዱሳን በሙሉ ከእ ግዚአብሔር ጋር የሚኖሩበት መጨረሻው እስከሚመጣ ᵉበትጋት ᶠበመፀለይ ይጸናል።

፳፫ እነሆ፣ ልጄ፣ ከላማናውያን ጋር ለመ ዋጋት ወዲያው ካልሄድኩ በድጋሚ እፅፍ ልሃለሁ። እነሆ፣ የዚህ ሀገር ወይም የኔፋ ውያን ᶜኩራት፣ ንሰሃ ካልገቡ በቀር እንደ ሚጠፉ አረጋግጦአል።

፳፬ ልጄ ንሰሃ ይመጣላቸው ዘንድ ለእ ነርሱ ፀልይላቸው። ነገር ግን እነሆ፣ መን ፈስ ከእነርሱ ጋር መስራቱን ᶜእንዳያቆም እፈራለሁ፤ እናም በዚህች ምድርም ደግሞ ሁሉንም ከእግዚአብሔር የመጣውን ኃይ ልና ስልጣን ለማናናቅ ይፈልጋሉ፤ እናም እነርሱም መንፈስ ቅዱስን ᵃካደዋል።

፳፭ እናም ልጄ፣ ታላቁን እውቀት አንቀ በልም ካሉ በኋላ፣ እነርሱ በነቢያት የተነገ ሩትን ትንቢቶች፣ እናም ደግሞ በአዳኛችን በራሱ የተነገሩትን ቃላት ይፈፅሙ ዘንድ በፍጥነት መጥፋት አለባቸው።

፳፮ ልጄ እስከምፅፍልህ ወይንም በድጋሚ እስከማገኝህ ድረስ ደህና ሁን። አሜን።

ሞርሞን ለልጁ ሞሮኒ የፃፈው ሁለተኛው ደብዳቤ።

ምዕራፍ ፱ አጠቃሎ የያዘ።

ምዕራፍ ፱

ኔፋውያን እናም ላማናውያን ነውረኛ እና የረከሱ ናቸው—እነርሱም እርስ በርሳቸው ስቃይን እናም ግድያን ይፈፅማሉ—ሞር ሞንም ፀጋ እና ቸርነት ለዘለዓለም በሞሮኒ ላይ እንዲሆን ፀለየ። ፬፻፷ ዓ.ም. ገደማ።

፩ የተወደድክ ልጄ እስካሁን በህይወት ያለሁ መሆኔን ታውቅ ዘንድ በድጋሚ ይህ ንን ፃፍኩልህ፤ ነገር ግን አሳዛኝ ስለሆነው ነገር በመጠኑ እፅፋለሁ።

፪ እነሆም፣ ከላማናውያን ጋር ድልን ያላገኘንበት አሰቃቂ የሆነ ውጊያ አድ ርጌ ነበር፤ እናም አርኬአንቱስ፣ ደግሞም ሉራም፣ እና ኤምሮን በጎራዴው ወደቁ፤ አዎን፣ እናም በርካታ የተመረጡ ጀግኖ ቻችንን አጥተናል።

፫ እናም እንግዲህ እነሆ ልጄ፣ ላማናው ያን እነዚህን ሰዎች ያጠፉአቸዋል ብዬ እፈ ራለሁ፤ ምክንያቱም እነርሱ ንሰሀ አልገ ቡም እናም ሰይጣንም ዘወትር እርስ በእር ሳቸው እንዲበጣበጡ እያደረጋቸው ነውና።

፬ እነሆ፣ እኔም ያለማቋረጥ ከእነርሱ ጋር እየሰራሁ ነኝ፣ የእግዚአብሔርንም ቃል ᵐበኃይለ ቃል ስናገር እነርሱ ይንቀጠቀ ጣሉ እናም ይቆጡኛል፤ እናም በኃይለ ቃል ባልተናገርኳቸውም ጊዜ በቃሉ ላይ ልባቸውን ያጠጥራሉ፤ ስለሆነም የጌታ መንፈስ ከእነርሱ ጋር መሆኑን ᵃያቆማል ብዬ እፈራለሁ።

፭ እነርሱም እጅግ በኃይል ተቆጥተው ስለነበር ሞትንም ቢሆን የማይፈሩ መስለ ውኛል፤ እርስ በርሳቸውም የነበራቸውን ፍቅር አጥተዋል፤ እናም ለፀብና ያለማቋ ረጥ ለመበቀል ᵐጥማት አላቸው።

፮ እናም እንግዲህ፣ የተወደድክ ልጄ፣

፳፭ሐ ት. እና ቃ. ፫፮፡ ፶፪።
ቅ.መ.መ. የኃጢያት ስርየት።
፳፮ ሀ ቅ.መ.መ. ገር፣ ገርነት።
ለ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
ሐ ቅ.መ.መ. አፅናኝ።
መ ቅ.መ.መ. ተስፋ።
ሠ ፩ ጴጥ. ፩፡ ፳፪፤
፩ ኔፊ ፲፩፡ ፳፪–፳፭።
ረ ቅ.መ.መ. ቅዱሳን።
ሰ ቅ.መ.መ. ትጋት።
ሸ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
፳፮ ሀ ት. እና ቃ. ፴፯፡ ፴፱።
ቅ.መ.መ. ኩራት።
፳፯ ሀ ሞር. ፭፡ ፲፯።
ለ አልማ ፴፱፡ ፮።
ቅ.መ.መ. ይቅርታ የሌለው ኃጢያት።
፴ ፴ ሀ ፪ ኔፊ ፩፡ ፳፮–፳፯፤
ት. እና ቃ. ፲፯፩፡ ፶፩–፶፫።
ለ ት. እና ቃ. ፩፡ ፴፫።
፭ ሀ ሞር. ፱፡ ፲፩–፲፪።

እነርሱ ልባቸውን ቢያጠጥሩም እኛ ᵐተግ
ተን እንስራ፤ ᵃመስራት ካቆምን እንኮነናለ
ንና፤ የፅድቅ ጠላት የሆነውን ሁሉ እናሸንፍ
ዘንድ፣ እናም ነፍሳችንን በእግዚአብሔር
መንግስት እናሳርፍ ዘንድ፣ በዚህ በጭቃ
ሰውነታችን የምናከናውነው ስራ አለንና።

፲ እናም አሁን ስለዚህ ህዝብ ስቃይ በመ
ጠኑ እፅፋለሁ። ከአሞሮን ባገኘሁት እው
ቀት መሠረት እነሆ፣ ላማናውያን ከሼሪዛ
ግንብ የወሰዱአቸው ብዙ እስረኞች አሉአ
ቸው፤ ወንዶችም፣ እናም ሴቶችም፣ እናም
ልጆችም ነበሩ።

፲፩ እናም የእነዚህ ሴቶችና የልጆቹ ባሎ
ችንና አባቶች ተገድለዋል፤ እናም ሴቶችን
የባሎቻቸውን ስጋ እንዲበሉ እናም ልጆ
ችም የአባቶቻቸውን ስጋ እንዲበሉ አደረ
ጉአቸው፤ እናም ከጥቂት በስተቀር ምንም
ውኃ አይሰጡአቸውም ነበር።

፲፪ እናም ላማናውያን ይህ ታላቅ እርኩ
ሰት ቢኖርባቸውም በሞሪያንቱም ካሉት
ከኛ ህዝብ ጥፋት አይበልጥም። እነሆ ብዙ
የላማናውያን ሴት ልጆችም በምርኮ ወስ
ደው ነበርና፤ እናም ከሁሉም ነገሮች በላይ
የተወደሰ እና የተከበረ፣ እንዲሁም ᵐድን
ግልነታቸውን እና ᵃምግባረ ጥሩነታቸው
ከወሰዱባቸው በኋላ—

፲፫ እናም ይህን ካደረጉ በኋላ፣ ጭካኔ በተ
ሞላበት ሁኔታ ገደሉአቸው፤ ሰውነታቸ
ውንም እስከሚሞቱ አሰቃዩአቸው፤ እናም
ይህንን ካደረጉ በኋላ፣ ልባቸው ጠጣር በመ
ሆኑ እንደዱር አውሬ ስጋቸውን በጨቁአ
ቸው፤ እናም ይህንንም ያደረጉት ጀግንነ
ታቸውን ለማሳየት ነበር።

፲፬ አቤቱ የተወደድክ ልጄ፣ እንደዚህ
አይነቶቹ ሰዎች እንዴት ያልሰለጠኑ ሊሆኑ
ተቻላቸው—

፲፭ (እናም ደግሞ ጥቂት ዓመታት አለፉ፣
እናም ሰዎቹም የሰለጠኑ እናም መልካም
ሰዎች ነበሩ)

፲፮ ነገር ግን አቤቱ ልጄ ከእንደዚህ ዓይ
ነት ህዝብ ደስታ እንዴት በእርኩስነት ሊገኝ
ይችላል—

፲፯ እግዚአብሔርስ እጆቹን በፍርድ ከእኛ
ላይ ᵐአያነሳም ብለን እንዴት እንጠብቃለን?

፲፰ እነሆ፣ ልቤ፥ ለዚህ ህዝብ ወዮለት ብላ
ታለቅሳለች። አቤቱ እግዚአብሔር ቅጣ
ትህን ፈፅም እናም ኃጢአታቸውን እናም
እርኩሰቶቻቸውን ከፊትህ ደብቅላቸው!

፲፱ እናም በድጋሚ ልጄ፣ በሼሪዛ የቀሩ
ብዙ ᵐባልቴቶች እና ሴት ልጆቻቸው
አሉ፤ እናም እነዚያን ላማናውያን ያልወ
ሰዷቸውን ስንቆች፤ እነሆ፣ የዜኔፊ ወታ
ደሮችም ወሰዱአቸው እናም በየደረሱበት
ስፍራም ምግብ ፈልገው እንዳያገኙ ተዉ
አቸው፤ እናም በጉዞአቸውም ብዙ አረጋ
ውያን ሴቶች እራሳቸውን ሳቱ እናም ሞቱ።

፲፲ እናም ከእኔም ጋር የነበሩት ወታደሮች
ደካሞች ናቸው፤ እናም የላማናውያን ወታ
ደሮች በሼሪዝ እና በእኔ መካከል ናቸው፤
ወደ ᵐአሮን ወታደር የሸሹት በሙሉ በእነ
ርሱ ጨካኝነት ወድቀዋል።

፲፳ አቤቱ የህዝቤ ጥፋት እንዴት ይገር
ማል! እነርሱም ምህረትም ሆነ ስርዓት የላ
ቸውም። እነሆ፣ ነገር ግን እኔ ወንድ ነኝ፣
እናም የወንድ ጥንካሬም ብቻ ነው ያለኝ፣
እናም ከዚህ በኋላም ትዕዛዜን እንዲቀበሉ
ላስገድዳቸው አልችልም።

፲፱ እናም በብልግናቸው ጠንካሮች ሆኑ፤
እናም በሁሉም ነገር ጨካኝ በመሆናቸው
ህፃናትንም ሆነ ሽማግሌዎችን አላስተረ
ፉም፤ መልካም ከሆነው በስተቀር በሁ
ሉም ነገር ይደሰታሉ፤ እናም የሴቶቻችን
እናም የልጆቻችን ስቃይ በምድር ገፅታ ላይ
ከነበረው ከማንኛውም የበለጠ ነው፤ አዎን፣
በአንደበት ለመናገርም ሆነ ለመፃፍ የሚ
ቻል አይደለም።

፳ እናም እንግዲህ ልጄ፣ በዚህ አስከፊ
በሆነ ሁኔታ ከዚህ በላይ አልቆይም። እነሆ፣

፲ ᵐ ቅ.መ.መ. ትጋት።
ᵃ ያዕቆ. ፩፡፲፱፤ ኢኖስ ፩፡፳።

ᵐ ቅ.መ.መ. ሁለንተና።
ᵃ ᵐ ቅ.መ.መ. ንጹህነት።
ᵃ ቅ.መ.መ. በጎነት።

ᵐ ᵃ አልማ ፲፡፳፫።
ᵐ ᵃ ᵐ ቅ.መ.መ. ባል የሞተባት።
ᵐ ᵃ ᵐ ሞር. ፪፡፱።

አንተ የህዝብህን ኃጢያት ታውቃለህ፤ እነ
ርሱም መሰረታዊ መርሆች እንደሌላቸው
እናም ስሜት እንደሌላቸው ታውቃለህ፤
እናም ክፋቶቻቸውም ከላማናውያን [ሀ]በላይ
ናቸው።

፳፩ እነሆ ልጄ፣ እግዚአብሔርም ይመታ
ኛል ብዬ በመፍራቴ እነርሱን ብቁ ናቸው
ብዬ ለመመስከር አልችልም።

፳፪ ነገር ግን እነሆ፣ ልጄ፣ ለእግዚአብ
ሔር ስለአንተ እመሰክራለሁ፣ እናም አን
ተም እንደምትድን በክርስቶስ እምነት
አለኝ፤ እናም ህዝቡም ወደ እርሱ ሲመ
ለሱ ወይንም ፈፅመው ሲጠፉ እንድትመ
ሰክር እግዚአብሔርም ህይወትህን [ለ]እንዲያ
ተርፍ እፀልያለሁ፣ [ሐ]ንስህ ካልገቡ እና ወደ
እርሱ ካልተመለሱ መጥፋት እንዳለባቸው
አውቃለሁና።

፳፫ እናም በልቦቻቸው ሙሉ ፈቃድ፣
ደም እና [ሀ]በቀል [ለ]መሻታቸው፣ ከጠፉ
ጥፋታቸው እንደ ያሬዳውያን ይሆናል።

፳፬ እናም የሚጠፉም ከሆነ፣ ብዙ ወን
ድሞቻችን ከላማናውያን ጋር ለመቀላቀል
[ሀ]እንደሔዱ እናም ከዚህም ደግሞ የበለጡ
ብዙዎች እንደሚሄዱ እናውቃለን፤ ስለ
ሆነም፣ አንተ ከተረፍክ እናም እኔ ከጠ
ፋሁ እናም አንተን ካላየሁ ነገሮችን በመ
ጠኑ ጻፍ፤ ነገር ግን ለአንተ [ሀ]የምሰጥህ
ቅዱስ መዛግብት ስላሉኝ በቅርቡ እንደማ
ይህ ተስፋ አለኝ።

፳፭ ልጄ በክርስቶስ የታመንክ ሁን፤
እናም የፃፍኳቸውም ነገሮች አንተን ለሞት
እስከሚያደርሱ አያሳዝኑህ፤ ነገር ግን ክር
ስቶስ ከፍ ያድርግህ፣ እናም [ሀ]ስቃዩ፣ እናም
ሞቱ፣ እናም ሰውነቱን ለአባታችን ማሳ
የቱ፣ እናም ምህረቱ እናም ፅናቱ፣ እናም
ለክብሩ እናም [ለ]ለዘለዓለማዊ ህይወት ያለው
ተስፋ ለዘለዓለም [ሐ]በአዕምሮህ ይኑር።

፳፮ እናም በሰማያት ዙፋኑ ከፍ ያለው
የእግዚአብሔር አብ፣ እናም ሁሉም ነገር
በእርሱ የሚገዙ እስከሚሆን ድረስ በኃይሉ
[ሀ]በቀኝ እጅ በኩል የተቀመጠው የጌታችን
የኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋ ለዘለዓለም ከአንተ
ጋር ይሁን እናም ይኑር። አሜን።

ምዕራፍ ፲

*የመፅሐፈ ሞርሞን ምስክርነት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይመጣል—ለታማኞች የመ
ንፈስ ስጦታዎች ይሰጣቸዋል—መንፈሳ
ዊው ስጦታዎች ዘወትር እምነትን ይከ
ተላል—የሞሮኒ ቃላት ከምድር ይናገ
ራሉ—ወደ ክርስቶስ ኑ፤ በእርሱም ፍፁ
ማን ሁኑ፣ እናም ነፍሳችሁን አንፁ።
ፀ.ዓ.ል. ፳ ዓ.ም. ገደማ።*

፩ አሁን እኔ ሞሮኒ፣ መልካም የመሰለ
ኝን በመጠኑ እፅፋለሁ፤ ለወንድሞቼ [ሀ]ለላ
ማናውያንም እፅፋለሁ፤ እናም ስለክርስቶስ
መምጣት ምልክት ከተሰጠ አራት መቶ ሃያ
ዓመት ማለፉን እንዲያውቁ እፈልጋለሁ።

፪ እናም እናንተን በጥብቅ በመምከር
ጥቂት ከተናገርኳችሁ በኋላ እነዚህን መዛ
ግብት [ሀ]አትማቸዋለሁ።

፫ እነሆ፣ እነዚህን ነገሮች በምታነቡበት
ጊዜ፣ ይህን እንድታነቡ በእግዚአብሔር
ጥበብ ከሆነ፣ ጌታም ለሰው ልጆች ከአዳም
መፈጠር ጀምሮ እነዚህን ነገሮች እስከም
ትቀበሉአቸው ጊዜ ድረስ ምን ያህል መሃሪ
እንደነበረ እንድታስታውሱ በጥብቅ እመክ
ራችኋለሁ፤ እናም [ሀ]በልባችሁ ይህን [ለ]አሰ
ላስሉ።

፳ ሀ ሐሌ. ፯ ፡ ፴፬–፴፭።
፳፪ ሀ ሞር. ፳ ፡ ፫።
ለ ሚል. ፫ ፡ ፯ ፤
ሐሌ. ፲፫ ፡ ፲፩ ፤
፫ ኔፊ ፲ ፡ ፲ ፤ ፳፬ ፡ ፯።
፳፫ ሀ ኤተር ፲፭ ፡ ፲፭–፴፩።
ለ ሞር. ፪ ፡ ፲፩–፲፪።
፳፬ ሀ አልማ ፵፭ ፡ ፲፬።
ለ ሞር. ፯ ፡ ፯።
፳፭ ሀ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ዋጋን
መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ።
ለ ቅ.መ.መ. የዘለዓለም
ህይወት።
ሐ ቅ.መ.መ. አዕምሮ።
፳፯ ሀ ሉቃ. ፳፪ ፡ ፳፬ ፤
የሐዋ. ፯ ፡ ፶፭–፶፮ ፤
ሞዛያ ፭ ፡ ፱ ፤
አልማ ፳፯ ፡ ፲፪።
፲ ፩ ሀ ት.እና ቃ. ፲ ፡ ፵፰።
፪ ሀ ሞር. ፳ ፡ ፬ ፣ ፲፫–፲፬።
ቅ.መ.መ. ቅዱሳት
መጻህፍት—እንደሚመጡ
የተተነበዩ ቅዱሣት
መጻህፍት።
፫ ሀ ዘዳግ. ፯ ፡ ፮–፯።
ለ ዘዳግ. ፲፩ ፡ ፲፰–፲፱።
ቅ.መ.መ. ማሰላሰል።

፬ እናም እነዚህንም ነገሮች በምትቀበሉበት ጊዜ፣ እነዚህ ነገሮች [ሀ]ሀሰት እንደሆኑ ዘለዓለማዊ አብ እግዚአብሔርን በክርስቶስ ስም [ለ]እንድትጠይቁት አጥብቄ እመክራችኋለሁ፤ እናም [ሐ]በቅን ልባችሁ፤ [መ]ከእውነተኛ ፍላጎት፣ በክርስቶስ [ሠ]አምናችሁ ከጠየቃችሁት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል [ረ]እውነቱን [ሰ]ይገልፅላችኋል።

፭ እናም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሁሉንም ነገር [ሀ]እውነታ [ለ]ታውቁታላችሁ።

፮ እናም መልካም የሆነ ማንኛውም ነገር ጻድቅ እና እውነተኛ ነው፤ ስለሆነም፣ መልካም የሆነ ማንም ክርስቶስን አይክድም፤ ነገር ግን እርሱ መሆኑን ያረጋግጣል።

፯ እናም እርሱ መሆኑንም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ታውቃላችሁ፤ ስለሆነም፣ የእግዚአብሔርን ኃይል እንዳትክዱ በጥብቅ እመክራችኋለሁ፤ ምክንያቱም እርሱ፣ በሰው ልጆች እምነት [ሀ]መሰረት፣ በኃይሉ ዛሬም እንዲሁም ነገም፣ እናም እስከዘለዓለም በአንድ አይነት ይሰራልና።

፰ እናም በድጋሚ ወንድሞቼ፣ የእግዚአብሔር [ሀ]ስጦታዎች እንዳትክዱአቸው አጥብቄ እመክራችኋለሁ፣ ብዙ ናቸውና፤ እና እነርሱም የሚመጡት ከአንድ እግዚአብሔር ነው። እናም እነዚህ ስጦታዎች የሚገለጡበት [ለ]የተለያዩ መንገዶች አሉ፤ ነገር ግን ሁሉን በሁሉ የሚያደርገው እግዚአብሔር አንድ ነው፤ እናም ለሰው በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ መገለጥ ለጥቅሙ ይሰጠዋል።

፱ እነሆም፣ ለአንዱ የጥበብን ቃል [ሀ]ያስተምር ዘንድ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ [ለ]ይሰጠዋል።

፲ እናም ለሌላው፣ ለእርሱም በዚያው መንፈስ የእውቀትን ቃል ያስተምር ዘንድ ይሰጠዋል።

፲፩ እናም ለሌላው እጅግ ታላቅ [ሀ]ዕምነት፤ ለሌላውም በዚያው መንፈስ [ለ]የመፈወስ ስጦታ ይሰጠዋል፤

፲፪ እናም በድጋሚ፣ ለሌላው፣ ታላላቅ [ሀ]ተአምራትን ያደርግ ዘንድ ይሰጠዋል፤

፲፫ እናም በድጋሚ፣ ለሌላው ስለሁሉም ነገሮች ትንቢት እንዲናገር ይሰጠዋል፤

፲፬ እናም በድጋሚ፣ ለሌላው፣ መላዕክትን የማየት እናም የመንፈስ አገልጋይነት ይሰጠዋል፤

፲፭ እናም በድጋሚ፣ ለሌላው ሁሉንም ዓይነት ልሳን ይሰጠዋል፤

፲፮ እናም በድጋሚ፣ ለሌላው፣ [ሀ]ቋንቋዎችን እናም የተለያየ ዓይነት ልሳን የተነገሩትን መተርጎም ይሰጠዋል።

፲፯ እናም እነዚህ ሁሉ ስጦታዎች የሚመጡት በክርስቶስ መንፈስ አማካኝነት ነው፤ እናም እነርሱም ለእያንዳንዱ ሰው ለብቻው እያካፈለ እንደፈቃዱ ይመጣሉ።

፲፰ እናም የተወደዳችሁ ወንድሞቼ መልካም ስጦታ [ሀ]ሁሉ ከክርስቶስ እንደሚመጣ እንድታስታውሱ አጥብቄ እመክራችኋለሁ።

፲፱ እናም የተወደዳችሁ ወንድሞቼ እርሱ ዛሬም እናም ነገም እናም ለዘለዓለም [ሀ]አንድ አይነት እንደሆነ፣ እናም የተናገርኳቸው መንፈሳዊ የሆኑት እነዚህ ስጦታዎች በሙሉ ምድር እስካለች የሰው ልጆች [ለ]እምነት ካላጡ በስተቀር ፈፅሞ መኖራቸ

፬ ሀ ፩ ኔፊ ፲፫፥፴፱፤ ፲፬፥፴፤
ሞዛያ ፩፥፮፤
ኤተር ፬፥፲–፲፩፤ ፭፥፫።
ለ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
ሐ ቅ.መ.መ. ታማኝ፣
ታማኝነት።
መ ያዕ. ፩፥፭–፯፤
ሞሮኒ ፯፥፱።
ሠ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
ረ ቅ.መ.መ. እውነት።
ሰ ቅ.መ.መ. ራዕይ።
፭ ሀ ዮሐ. ፰፥፴፪።
ለ ት. እና ቃ. ፴፭፥፲፱።
ቅ.መ.መ. ምስክርነት፤
የመለየት ስጦታ።
፯ ሀ ፪ ኔፊ ፲፥፲፯–፲፱።
፰ ሀ ቅ.መ.መ. የመንፈስ
ስጦታዎች።
ለ ት. እና ቃ. ፵፮፥፲፭።
፱ ሀ ት. እና ቃ. ፹፰፥፸፯–፸፱፣
፻፲፰።
ለ ፩ ቆሮ. ፲፪፥፰–፲፩፤
ት. እና ቃ. ፵፮፥፰–፳፱።
፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
ለ ቅ.መ.መ. መፈወስ፣
ፈውሶች።
፲፪ ሀ ቅ.መ.መ. ተአምራት።
፲፮ ሀ ቅ.መ.መ. የልሳኖች ስጦታ።
፲፰ ሀ ያዕ. ፩፥፲፯።
፲፱ ሀ ዕብ. ፲፫፥፰።
ለ ሞሮኒ ፯፥፴፯።

ውን እንደማያቆሙ እንድታስታውሱ አጥ
ብቁ እመክራችኋለሁ።
፳ ስለሆነም፣ እምነት ሊኖር ይገባል፤
እናም ᵐእምነት ካለ ተስፋም ደግሞ ሊኖር
ይገባል፤ እናም ተስፋም ደግሞ ካለ ልግስና
መኖር አለበት።
፳፩ እናም እናንተ ᵐልግስና ከሌላችሁ በእ
ግዚአብሔር መንግስት በምንም መንገድ
ልትድኑ አይቻላችሁም፤ ወይም እምነት
ከሌላችሁ በእግዚአብሔር መንግስት ለመ
ዳን አትችሉም፤ ወይም ተስፋም ከሌላችሁ
ለመዳን አይቻላችሁም።
፳፪ እናም ተስፋ ከሌላችሁ በተስፋ
መቁረጥ ላይም መሆን አለባችሁ፣ እናም
ተስፋ መቁረጥም የሚመጣው በክፋት ነው።
፳፫ እናም ክርስቶስ ለአባቶቻችን በእው
ነት እንዲህ ሲል ተናግሯቸዋል፥ እናንተም
ᵐእምነት ካላችሁ ለእኔ አስፈላጊ የሆነውን
ለማድረግ ይቻላችኋል።
፳፬ እናም አሁን እስከአለም ጫፍ ላሉት
ሁሉ እንዲህ ስል እናገራለሁ—የእግዚ
አብሔር ኃይልና ስጦታ በእናንተ መካ
ከል መሆኑን የሚያቆምበት ቀን ከመጣ፣
ይህም የሚሆነው ᵐእምነት በማጣት ᵃምክ
ንያት ነው።
፳፭ እናም እንዲህ ከሆነ ለሰው ልጆች
ወዮላቸው፤ ከእናንተ መካከል አንድም
እንኳን ቢሆን መልካም የሚሰራ ᵐምንም
የለምና። ከመካከላችሁ መልካምን የሚያ
ደርግ አንድ እንኳን ቢኖር፣ እርሱም በእግ
ዚአብሔር ኃይልና ስጦታ ይሰራል።
፳፮ እናም እነዚህን ነገሮች ለሚያስወግ
ዱት እናም ለሚሞቱ ወዮላቸው፣ ምክን
ያቱም ᵐከነኃጢአታቸው ᵃይሞታሉ እናም
በእግዚአብሔር መንግስት አይድኑምና፤
እናም እኔም የተናገርኩት በክርስቶስ ቃል
መሰረት ነው፤ እናም ሀሰትን አልተናገር
ኩም።
፳፯ እናም እነዚህን ነገሮች እንድታስታ
ውሱ አጥብቄ እመክራችኋለሁ፤ እኔ ሀሰት
እንዳልተናገርኩ የምታውቁበት ቀን በፍጥ
ነት ይመጣል፣ በእግዚአብሔር ፍርድ ወን
በርም ታዩኛላችሁና፤ እናም ጌታ አምላክ
እንዲህ ሲል ይናገራችኋል፥ ከሙታን ᵐእን
ደሚጮህ፣ አዎን፣ አንድ ሰው ᵃከመሬት
እንደሚናገር በዚህ ሰው የተፃፉትን ᵃᵃቃላት
ለእናንተ አላወጅኩላችሁምን?
፳፰ ትንቢቶች ይፈፀሙ ዘንድ እነዚ
ህን ነገሮች ለእናንተ አውጀአለሁ። እናም
እነሆ፣ እነርሱም ከዘለዓለማዊው አምላክ
አንደበት ይወጣሉ፤ እናም ቃሉም ከትው
ልድ ወደ ትውልድ ᵐያፏጫል።
፳፱ እናም እግዚአብሔርም የፃፍኩት
እውነት እንደሆነ ያሳያችኋል።
፴ እናም በድጋሚ ወደ ክርስቶስ ᵐእንድ
ትመጡ፣ እናም እያንዳንዱን መልካሙን
ስጦታ እንድትይዙ፣ እናም ክፉውን ስጦታ
ወይም እርኩስን ነገር ᵃእንዳትነኩ አጥብቄ
እመክራችኋለሁ።
፴፩ እናም እስራኤል ሆይ ᵐንቂ ከመ
ሬት ተነሽ፤ አዎን፣ እናም አቤቱ ᵃየፅዮን
ሴት ልጅ፣ የሚያምረውን መጎናፀፊያሽን
ልበሺ፤ እናም ከዚህም በኋላ ᵃᵃእንዳትቀላ
ቀሊ፣ የዘለዓለማዊ አባት ለአንቺ፣ አቤቱ
የእስራኤል ቤት፣ የገባው ቃል ኪዳን ይሟ
ላም ዘንድ ᵐካስማዎችሽን ᵐᵐአጥብቂ እናም
ወሰንሽንም ለዘለዓለም አስፊ፤ ከእንግዲ
ህም አታፍሪም።

፳ ሀ ኤተር ፲፪፡፲–፴፯።
፳፩ ሀ ፩ ቆሮ. ፲፫፡
ሞሮኒ ፯፡፩፣ ፴፪–፴፰።
ቅ.መ.መ. ልግስና።
፳፫ ሀ ሞሮኒ ፯፡፴፫።
፳፬ ሀ ቅ.መ.መ. አለማመን።
ለ ሞሮኒ ፯፡፴፯።
፳፭ ሀ ጆ.ስ.ት. መዝ. ፲፡፩–፯
(ተጨማሪ)፤
ሮሜ ፫፡፲–፲፪።
፳፮ ሀ ዮሐ. ፳፡፳፩።
ለ ሕዝ. ፲፰፡፳፯–፳፯፤
፩ ኔፊ ፲፭፡፴፪–፴፫፤
ሞዛያ ፲፭፡፳፯።
፳፯ ሀ ፪ ኔፊ ፫፡፲፱–፳፣ ፳፯፡፲፫፣
፴፫፡፲፫፣
ሞር. ፱፡፴።
ለ ኢሳ. ፳፱፡፱–፲፩።
ሐ ፪ ኔፊ ፴፫፡፲–፲፩።
፳፰ ሀ ፪ ኔፊ ፳፱፡፪።
፴ ሀ ፩ ኔፊ ፯፡፱፣
ሞር. ፱፡፳፯፣
ኤተር ፭፡፭።
ለ አልማ ፭፡፶፯።
፴፩ ሀ ኢሳ. ፶፪፡፩–፪።
ለ ቅ.መ.መ. ፅዮን።
ሐ ኤተር ፲፫፡፳።
መ ቅ.መ.መ. ካስማ።
ሠ ኢሳ. ፶፬፡፪።

፴፪ አዎን፣ ወደ ክርስቶስ ᵐኑ፣ እናም በእ
ርሱም ᵃፍፁማን ሁኑ፣ እናም ኃጢአተኝ
ነትን በሙሉ ለእራሳችሁ ካዱ፤ እናም
ለራሳችሁ ኃጢአተኝነትን በሙሉ ከካዳ
ችሁ፣ እናም በሙሉ ኃይላችሁ፣ አዕምሮ
አችሁ እና ጉልበታችሁ እግዚአብሔርን
ᵇከወደዳችሁ፣ ፀጋው ለእናንተ ይበቃች
ኋል፣ በፀጋውም በክርስቶስ ፍፁም ትሆና
ላችሁ፤ እናም በእግዚአብሔር ᶜፀጋ በክ
ርስቶስ ፍፁም ከሆናችሁ፣ የእግዚአብሔ
ርን ኃይል በምንም መልኩ አትክዱትም።

፴፫ እናም በድጋሚ፣ በእግዚአብሔር
ፀጋ በክርስቶስ ፍፁማን ከሆናችሁ፣ እናም
ኃይሉን ካልካዳችሁ፣ በእግዚአብሔር ፀጋ፣
ለኃጢአታችሁ ᵃስርየት አብ በገባው ቃል
ኪዳን ውስጥ ባለው በክርስቶስ ᵃደም መፍ
ሰስ ያለ እንከን ᵇቅዱስ ትሆኑ ዘንድ በክር
ስቶስ ᶜትቀደሳላችሁ።

፴፬ እናም አሁን ሁላችሁንም እሰናበታ
ችኋለሁ። ᵃመንፈስና ስጋዬም በአንድነት
ᵃእስኪገናኝ፣ እናም ለህያዋን እና ለሙታን
ዘለዓለማዊ ᵇዳኛ በሆነው በታላቁ ᶜያህዌህ
ᶜአስደሳቹ የፍርድ ወንበር ፊት እናንተን
ለመገናኘት ድል አድርጌ ወደ ᶜሰማይ እስ
ከምመጣ ድረስ፣ በቅርብ ወደ እግዚአብ
ሔር ᵃገነት ᵇለማረፍ እሄዳለሁ። አሜን።

፴፪ ሀ ማቴ. ፲፩፡ ፳፰፤
፪ ኔፊ ፳፯፡ ፴፫፤
ያዕቆ. ፩፡ ፯፤
ኦምኒ ፩፡ ፳፯።
ለ ማቴ. ፭፡ ፴፰፤
ፊ ኔፊ ፲፪፡ ፴፰።
ቅ.መ.መ. ፍጹም።
ሐ ት. እና ቃ. ፀ፡ ፪፤ ፶፱፡ ፭–፯።
መ ፪ ኔፊ ፳፭፡ ፳ፊ።
፴ፊ ሀ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ስርየት።
ለ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ዋጋን
መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ።
ሐ ቅ.መ.መ. ቅድስና።
መ ቅ.መ.መ. ቅድስና።
፴፬ ሀ ቅ.መ.መ. መንፈስ።
ለ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
ሐ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ
ክርስቶስ—ዳኛ።
መ ቅ.መ.መ. ያህዌህ።
ሠ ያዕቆ. ፯፡ ፲ፊ።
ረ ፩ ተሰ. ፬፡ ፲፯።
ሰ ቅ.መ.መ. ገነት።
ሸ ቅ.መ.መ. እረፍት።

የኋለኛው ቀን ቅዱሳን
የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን

ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች

ይህም ለነቢዮ ለጆሴፍ ስሚዝ
የተሰጡ ራእዮችን እና በእርሱ

ተተኪ በሆኑት የቤተክርስቲያኗ አመራር
ጥቂት የተጨመሩትን የያዘ ነው

ማውጫዎች

መግቢያ 5
የዘመን ቅድመ ተከተል. 9
ክፍሎች . . . . . ፪
አስተዳደሪያዊ አዋጆች. . . . . ፪፲፯፯

መግቢያ

ትምህርት እና ቃልኪዳኖች፣ በመጨረሻው ቀናት የእግዚአብሔርን መንግስት በምድር ላይ ለማቋቋም እና ለማስተዳደር መለኮታዊ ራእዮች እና የተነሳሱ ምሪት የተሰጡ አዋጆች ስብስብ ነው። ምንም እንኳን አብዛኞቹ ክፍሎች የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላትን የሚመለከቱ ቢሆኑም፣ መልእክቶቹ፣ ማስጠንቀቂያዎቹ፣ እና ማበረታቻዎቹ ለሰው ዘር በሙሉ ጥቅም ናቸው፤ እንዲሁም በሁሉም ቦታ ላሉት ሰዎች ሁሉ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን ድምጽ ለጊዜአዊ ጥቅማቸውና ለዘለአለማዊ ደህንነታቸው ሲናገራቸው እንዲሰሙ ግብዣን የያዙ ናቸው።

በዚህ ጥራዝ ውስጥ ያሉት አብዛኛዎቹ ራዕዮች በኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን የመጀመሪያ ነቢይ እና ፕሬዘደንት በነበረው በጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ፣ አማካኝነት የተሰጡ ነበሩ። ሌሎቹ በአመራሮቹ ውስጥ የእርሱ ተተኪ በሆኑት በኩል የተሰጡ ነበሩ (የክፍል ፤፴፭፣ ፤፴፯፣ እና ፤፴፰፣ እና የአስተዳደሪያዊ አዋጆች ፩ እና ፪ ርዕሶችን ተመልከቱ)።

መፅሐፈ ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች ይፋ ከሆኑት የቤተክርስቲያኗ ጽሁፎች፣ ከመጻሐፍ ቅዱስ፣ ከመጻሐፈ ሞርሞን፣ እና የታላቅ ዋጋ ዕንቁ፣ መካከል አንዱ ነው። ሆኖም ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች የጥንት ጽሁፍ ትርጉም ባለመሆኑ ልዩ ነው፣ ነገር ግን ዘመናዊ ግኝት ነው እናም በእግዚአብሔር በተመረጡ ነቢያት አማካኝነት ለቅዱስ ስራው ዳግመኛ መመለስ እና በእነዚህ ዘመናት የእግዚአብሔርን መንግስት በምድር ላይ ለማቋቋም የተሰጠ ነበር። በራዕዮቹ ውስጥ ለስላሳ ነገር ግን ፅኑ የሆነው የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ድምፅ በዘመን ፍጻሜ እንደገና ሲነገር ይደመጣል፤ እናም በዚህ ውስጥ የተጀመረው ስራ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ በቅዱሳን ነቢያት የተነገሩትን ቃላት በማሟላት እና በማስማማይ ለዳግም ምፅዓት መዘጋጀያ ነው።

ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ፣ በቫሮን፣ ዊንድሰር አውራጃ፣ ቨርሞንት ውስጥ በታህሳሥ ፭፲፣ ፲፰፻፩ (እ.አ.አ.) ተወለደ። በህይወቱ መጀመሪያ ላይ ከቤተሰቦቹ ጋር በምዕራብ ኒው ዮርክ በሚገኘው በዚህ ዘመን ማንቸስተር ወደሚባለው ሄደ። በዚያ አቅራቢያ እየኖረ ሳለ፣ በ፲፰፻፳ (እ.አ.አ.) ጸደይ፣ የአስራ አራት አመት ልጅ በነበረበት ወቅት ነበር የመጀመሪያውን ራእዩን የተቀበለው፣ በዚሁም በግል በእግዚአብሔር በዘለአለማዊው አባት፣ እና በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ተጎብኝቶ ነበር። በእዚህ ራእይ በአዲስ ኪዳን የተመሰረተችው እና ሙላተ ወን ጌልን ስታካሂድ የነበረችው እውነተኛይቷ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን በምድር ላይ እንደማትገኝ ተነግሮት ነበር። በብዙ መላዕክት ትምህርት እንዲሰጠው የተደረገበት ሌሎች መለኮታዊ መገለጦችም ተከትለው ነበር፤ እግዚአብሔር በምድር ላይ የተለየ ስራ ለእርሱ እንዳለው እናም በእርሱ አማካኝነት የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ዳግመኛ ወደ ምድር ተመልሳ እንደምትመጣ እንዲያይ ተደርጎ ነበር።

ከጊዜ በኋላም፣ ጆሴፍ ስሚዝ በመለኮታዊ እርዳታ መጽሐፈ ሞርሞንን እንዲተረጉምና እንዲያሳትም ይችል ዘንድ ተደርጎ ነበር። በዚያም ጊዜ እርሱ እና ኦሊቨር ካውድሪ በግን ቦት ፲፰፻፲፰፤ (እ.አ.አ.) በመጥምቁ ዮሐንስ ወደ አሮናዊ ክህነት ተሹመው ነበር (ት. እና ቃ. ፲፫ ተመልከቱ)፣ እናም ብዙም ሳይቆይ፣ በጥንቶቹ ኃዋሪያት በጴጥሮስ፣ በያዕቆብ እና በዮሐንስ ወደ መልከ ጼዴቅ ክህነት ተሹመው ነበር (ት. እና ቃ. ፳፯፡፣ ፲፪ ተመልከቱ)። ሌሎችም ሹመቶች ተከትለው ነበር፣ በዚህም በሙሴ፣ በኤልያስ እና በኤልያ፣ እንዲሁም በብዙ የጥንት ነቢያት የክህነት ቁልፎች ተስጥቷቸው ነበር (ት. እና ቃ. ፲፣ ፲፭፤ ፲፡፣ ፲፯ ተመልከቱ)። እነዚህ ሹመቶች በእርግጥም ለሰው ልጅ የመለኮታዊ ስልጣኖች ዳግመኛ የተመለሱባቸው ናቸው። በሚያዝያ ፮፣ ፲፰፻፴ (እ.አ.አ.) በመለኮታዊ አመራር መሰረት፣ ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ ቤተክርስቲያኗን አደራጀ፣ እንዲህም እውነተኛዋ የኢየሱስ ክርስቶስ

ቤተክርስቲያን ዳግመኛ በሰዎች መካከል እንደ እምነት ተቋም ወንጌልን ለማስተማር እና የደህንነት ስርዓቶችን ለማከናወን በስልጣን ስራዋን ጀመረች። (ት. እና ቃ. ፳፫ እና የታላቅ ዕንቁ ዋጋ፣ የጆሴፍ ስሚዝ—ታሪክ ፩ን ተመልከቱ)።

እነዚህ የተቀደሱ ራዕዮች ችግር በነበረበት ጊዜ የተቀበሉት የጸሎት መልስ ነበሩ፣ እናም የመጡትም እውነተኛ ሰዎች ከተሳተፉበት ከገሀዱ የህይወት ጉዳዮች ነበር። ነቢዩ እና ተባባሪዎቹ የመለኮታዊ ምሪትን ፈልገው ነበር፣ እና እነዚህ ራዕዮችም እነርሱ ይህን እንደተቀበሉ ያረጋግጣሉ። በራዕዮቹም፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ዳግመኛ መመለሱንና መገለጡን፣ እናም የዘመኑ ፍጻሜም የተቃረበ መሆኑን አንድ ሰው ለመመልከት ይችላል። የቤተክርስቲያኗ ከኒው ዮርክ እና ፔንሲላቫኒያ ወደ ኦሃዮ፣ ወደ ሚዙሪ፣ ወደ ኢሊኖይ፣ እና በመጨረሻም ወደ ታላቁ የምዕራብ አሜሪካ ሸለቆ ከነበራት የምዕራብ እንቅስቃሴ፣ እና በአሁኑ ዘመን ቅዱሳን ዕዮንን ለመገንባት የሞከሩበትን ትግል በእነዚህ ራዕዮች ውስጥ ተመልክተዋል።

ቀደም ብለው ያሉት አብዛኞቹ ክፍሎች ስለመጽሐፈ ሞሮሞን መተርጎም እና ህትመት የተመለከቱ ነገሮችን ያካተቱ ናቸው(ክፍል ፫፣ ፭፣ ፲፣ ፲፮፣ እና ፲፱ን ተመልከቱ)። ወደኋላ ያሉት አንዳንዶቹ ክፍሎች የነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተነሳሳ የመፅሐፍ ቅዱስ ትርጉም ስራውን የሚያንጸባርቁ ናቸው፣ በዚህም ጊዜ አብዛኞቹ ታላላቅ የትምህርት ክፍሎች ተገልጸዋል (ለምሳሌ ክፍል ፴፯፣ ፵፭፣ ፷፫፣ ፷፮፣ ፷፯፣ ፸፱፣ ፸፭ እና ፻፴፪ን ተመልከቱ፣ እያንዳንዳቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ጋር አንዳንድ ቀጥተኛ ግንኙነት አላቸው)።

በራዕዮቹ ውስጥ፣ የአምላክ ስነ-ፍጥረትን፣ የሰው ልጅ አጀማመርን፣ የሰይጣን መኖርን፣ የምድራዊ ህይወት ዓላማን፣ የመታዘዝን አስፈላጊነት፣ የንስሃን አስፈላጊነት፣ የመንፈስ ቅዱስ ስራዎችን፣ ደህንነትን የተመለከቱ ስርዐቶችና አፈጻጸሞችን፣ የምድር ዕጣ ፈንታን፣ ከትንሳኤ በኋላ የሚኖረው የሰው ልጅ ሁኔታ እና ፍርድን፣ የጋብቻ ግንኙነት ዘላለማዊነትን፣ እናም የቤተሰብ ዘለአለማዊ የመሆን ሁኔታን በሚመለከት መሰራታዊ ነገሮች መግለጫ በመስጠት የወንጌል ትምህርቶች ተገልጸዋል። እንደዚሁ ከኤጲስ ቆጳሳት፣ ከቀዳሚ አመራር፣ ከአስራ ሁለቱ ቡድን፣ እና ከሰባዎቹ እና ከሌሎች የአመራር ሹመቶች እና ቡድኖች ጥሪዎች ጋር በሂደት የተገለጸው የቤተክርስቲያኗ አስተዳደራዊ ቅርጾች ተገልጸዋል። በመጨረሻም ስለኢየሱስ ክርስቶስ መለኮታዊነት፣ ግርማው፣ ፍጹምነቱ፣ ፍቅሩ፣ እና የማዳን ኃይሉ የተሰጠው ምስክርነት ይህንን መጽሐፍ ለሰው ልጆች ቤተሰብ ታላቅ ዋጋ ያለው እና “ለቤተክርስቲያኗም ከምድር ሀብት ሁሉ የበለጠ ዋጋ እንዲኖረው” ያደርገዋል (የት. እና ቃ. ፷ መግቢያ ተመልከቱ)።

ራዕዮቹ በመጀመሪያ የተመዘገቡት በጆሴፍ ስሚዝ ጸሀፊዎች ነበር፣ እናም የቤተክርስቲያኗ አባላት በእጅ የተጻፉ ቅጂዎችን እርስ በእርስ በደስታ ይካፈሉ ነበር። ቋሚ መዝገብ ለመፍጠር፣ ጸሀፊዎች እነዚህን ራዕዮች ባልታተሙ የመዝገብ መፅሀፎች ውስጥ በቅጂ አዘጋጁ፣ እነዚህንም የቤተክርስቲያኗ መሪዎች ራዕዮችን ለማተም ለማዘጋጀት ተጠቀሙባቸው። ጆሴፍ ስሚዝ እና የመጀመሪያ የቤተክርስቲያኗ አባላት እነዚህን ራእዮች ቤተክርስቲያኗ በተመለከቱበት ሁኔታ ይመለከቷቸው ነበር፣ ህያው፣ ለውጥ የሚፈጥር፣ እና በተጨማሪ ራዕይ ለመጣራት የሚችል። ራዕዮችን በሚቀዱበት ጊዜ እና ለመታተም በሚዘጋጁበት ጊዜ ሳይታወቅ ስህተቶች ሊገቡባቸው እንደሚችሉም አውቀው ነበር። ስለዚህ፣ የቤተክርስቲያኗ ጉባኤ በ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.) ጆሴፍ ስሚዝ “በመንፈስ ቅዱስ በኩል ሊያገኛቸው የሚችላቸውን እነዚያን ጉድለቶች እና ስህተቶች እንዲያስተካክል” ጠየቁት።

ራዕዮች ከተገመገሙ እና ከተስተካከሉ በኋላ፣ የቤተክርስቲያኗ አባላት በምዙሪ ውስጥ የነቢዩን ብዙ የመጀመሪያ ራዕዮች የያዘውን፣ *A Book of Commandments for the Government of the Church of Christ* (በርዕስ መጽሐፈ ትእዛዛት ለክርስቶስ ቤተክሪስቲያን አስተዳደር) የሚባለውን መፅሀፍ ማተም ጀመሩ። ነገር ግን፣ በሀምሌ ፳፣ ፲፰፻፴፩ የ

(እ.አ.አ.) በጃክሰን የግዛት ክፍል ውስጥ የነበረውን የቅዱሳንን የእትመት ቢሮ በመደምሰሳ ቸው፣ ራዕዮችን ለማተም የተደረገው የመጀመሪያ ጥረት ቆመ።

የምዙሪ የእትመት ቢሮ እንደተደመሰሰ በሰሙበት ጊዜ፣ ጆሴፍ ስሚዝ እና ሌሎች የቤተ ክርስቲያኗ መሪዎች ራዕዮችን በከርትላንድ ኦሀዮ ለማተም ዝግጅት ጀመሩ። እንደገና ስህተ ቶችን ለማስተካከል፣ አባባሎችን ለመግለጽ፣ እና የቤተክርስቲያኗ ትምህርት እና ድርጅትን ለማሳወቅ፣ ጆሴፍ ስሚዝ የአንዳንድ ራዕዮችን ጽሁፎች የማረም ስራን በመቆጣጠር እነዚህን በ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.) እንደ *Doctrine and Covenants of the Church of the Latter Day Saints* (መጽሐፈ ትእዛዛት ለኋለኛው ቀን ቅዱሳን ቤተክሪስቲያን አስተዳደር) ለማሳተም አዘጋጀ። ጆሴፍ ስሚዝ የትምህርት እና ቃል ኪዳኖች ሌላ ቅጂ እኒድታተም ፈቃድ ሰጠ፣ ይህም የታተመው በ፲፰፻፴፪ (እ.አ.አ.) ከነቢዩ ሰማዕትነት ጥቂት ወሮች ካለፉ በኋላ ነበር።

የመጀመሪያዎቹ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን ለራዕዮቹ ታላቅ ዋጋ ሰጧቸው እናም እንደ እግዚአብሔር መልእክቶች ይመለከቷቸው ነበር። በ፲፰፻፴፭ (እ.አ.አ.)፣ አንድ ጊዜ፣ ብዙ የቤተክርስቲያኗ ሽማግሌዎች ጌታ በነፍሳቸው እነዚህ ራዕዮች እውነት እንደሆኑ እንደመሰከረ ላቸው የክብር ምስክራቸውን ሰጥተው ነበር። ይህ ምስክርነት በ፲፰፻፴፭ (እ.አ.አ.) የትምህርት እና ቃል ኪዳን ቅጂ ውስጥ በአስራ ሁለቱ ሐዋሪያት የተጻፈ ምስክር በመባል ታትሞ ነበር።

የመጽሐፈ ትምህርት እና ቃል ቃል ኪዳኖች እውነተኛነትን በተመለከተ የአስራ ሁለቱ ሐዋሪያት ምስክርነት

በቤተክርስቲያኗ ድምጽ ለዚህ ዓላማ በተመደበው ጆሴፍ ስሚዝ፣ ዳግማዊ፣ አማካኝነት ለቤተክርስቲያኗ የሰጠውን ትዕዛዛት፣ ይኸውም የጌታ ትእዛዛት መጽሐፍን በተመለከተ የምስክሮች ምስክርነት፥

ስለዚህ እኛ በአለም ለሚገኙ ለሰው ዘር በሙሉ፣ በምድር ገጽታ ላይ ላሉ ፍጡራን ሁሉ፣ እነዚህ ትእዛዛት በእግዚአብሔር ምሪት ለሰዎች ሁሉ ጥቅም እንደተሰጡ እና እውነት መሆናቸውን ጌታ ለነፍሳችን እንደመሰከረልን፣ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነትም እንዳፈሰሰልን ምስክርነታችንን ለመስጠት ፈቃደኞች ነን።

ጌታ እረዳታችን ሆኖ፣ ይህን ምስክርነት ለዓለም እንሰጣለን፤ እናም ለዓለም ምስክርነታችንን እድንሰጥ ይህንን ዕድል እድናገኝ የተፈቀደልን በእግዚአብሔር አብ፣ እና በልጁ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ነው፣ እኛም የሰው ልጆችም ሁል ጊዜ በዚህ ተጠቃሚ ይሆኑ ዘንድ ለጌታ እየጸለይን፣ በዚሁ ምስክርነት እጅግ በጣም ተደስተናል።

የአስራ ሁለቱ ስም ዝርዝር፥

ቶማስ ቢ ማርሽ	ኦርሰን ሀይድ	ዊሊያም ስሚዝ
ዴቪድ ደብሊው ፓተን	ዊሊያም ኢ መክለልን	ኦርሰን ፕራት
ብሪግሃም ያንግ	ፓርለይ ፒ ፕራት	ጆን ኤፍ ቦይንቶን
ሂበር ሲ ኪምቦል	ሉክ ኤስ ጆንሰን	ላይማን ኢ ጆንሰን

በተከታታይ የትምህርት እና ቃልኪዳኖች ቅጂዎች፣ ተጨማሪ ራእዮች እና ሌሎች መረጃዎች ብቁ በሆኑ ተሰብሳቢዎች ወይም በቤተክርስቲያኗ ጉባዔ ሲስተናገዱ እና ተቀባ ይነትን ሲያገኙ እንዲጨመሩ ተደርገዋል። በብሪገም ያንግ አመራር ስር በሽማግሌ ኦርሰን ፕራት የተዘጋጀው የ፲፰፻፵፭ (እ.አ.አ.) ቅጂ፣ ራዕዮችን በዘመን ቅድመ መከተል እና አዲስ ርዕሶችንና ታሪካዊ መግቢያዎች በመስጠት አዘጋጀ።

ከ፲፰፻፴፭ (እ.አ.አ.) ቅጂ ጀምሮ፣ ሰባት የመንፈሳዊ ትምህርት ትምህርቶች ተካተው

ነበር፤ *Lectures on Faith* (የእምነት ንግግሮች) የሚል ርዕስ ተሰጥቷቸው ነበር። እነዚህ ከ፲፰፻፴፪ (እ.አ.አ.) እስከ ፲፰፻፴፭ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ፣ ኦሃዮ፣ ለነቢያት ትምህርት ቤት መጠቀሚያ የተዘጋጁ ነበሩ። ለትምህርት እና መመሪያ ቢጠቅሙም፣ ከ፲፱፻፳፭ (እ.አ.አ.) ቅጂ ጀምሮ እነዚህ ንግግሮች ከትምህርትና ቃል ኪዳኖች ውስጥ እንዲወጡ ተደርገዋል፣ ምክንያ ቱም አጠቅላይ ቤተክርስቲያኗን በሚመለከት የተሰጡ ወይም የቀረቡ ራእዮች ስላልሆኑ ነው።

በትምህርት እና ቃል ኪድኖች የ፲፱፻፲፮ (እ.አ.አ.) በእንግሊዝኛው ቅጂ ውስጥ ሶስት መረጃዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ተጨምረው ነበር። እነዚህም የመታን ደህንነት መሰረታዊ መርሆችን የሚመሰርቱት ክፍሎች ፲፭፤ እና ፲፭፰፣ እና ያለዘር እና የቀለም ልዩነት ብቁ የቤተክርስቲያኗ ወንድ አባላት ለክህነት ለመሾም እንደሚችሉ ያስተዋወቀው የአስተዳደራዊ አዋጅ ፪ ነበሩ።

እያንዳንዱ የትምርት እና ቃል ኪዳን ቅጂ የድሮ ስህተቶችን አስተካክለዋል እና አዲስ መረጃዎችን፣ በተለይም በክፍል ርዕሶች የታሪክ ክፍሎችን፣ ጨምረዋል። የዚህ ጊዜ ቅጂ ቀናትን እና የቦታ ስምችን ያጣራል እና ሌሎችንም በተጨማሪ ያስተካክላል። እነዚህ ለውጦች የተደረጉት ጽሁፎችን ከብዙዎቹ ትክክለኛው ታሪካዊ መረጃዎች ጋር እንዲስማሙ ለማ ድረግ ነው። በዚህ አዲስ ቅጂ ውስጥ የሚገኙ ሌሎች ልዩ ነገሮችም ራዕዮች የተቀበለበትን ቦታዎች የሚያሳዮ ካርታዎችን የተከለሱበት፣ በተጨማሪውም የቤተክርስቲያኗን ታሪካዊ ፎርትዎች፣ ማጣቀሻዎችን፣ የክፍል ርዕሶችን፣ እና የርዕስ ማጠቃለያዎችን የተሻሻሉበት ነበሩ፤ ሁሉም ማሻሻያዎች የተደረጉት አንባቢዎች በትምህርት እና ቃል ኪዳኖች ውስጥ የተሰጡትን መልእክቶች እንዲረዱና እንዲደሰቱበት ለመርዳት ነበር። በክፍል ርዕሶች ውስጥ የሚገኙ መረጃዎችም የተወሰዱት ከቤተክርስቲያኗ ታሪክ ያልታተመ ፅሁፍ እና ከታተመው ከ*History of the Church* [የቤተክርስቲያኗ ታሪክ] (እነዚህም በርዕሶች ውስጥ አንድ ላይ የጆሴፍ ስሚዝ ታሪክ ተብለው ይጠራሉ) እና ከ *Joseph Smith Papers* [የጆሴፍ ሚዝ ፅሁፍ] ውስጥ ነበር።

የማውጫዎች የዘመን ቅድመ ተከተል

ቀን (እ.አ.አ.)		ቦታ	ክፍሎች
፲፰፻፸፫	መስከረም	ማንችስተር፣ ኒው ዮርክ	፪
፲፰፻፸፰	ሐምሌ	ሀርመኒ፣ ፔንሲላቬኒያ	፫
፲፰፻፸፱	የካቲት	ሀርመኒ፣ ፔንስልቬንያ	፬
	መጋቢት	ሀርመኒ፣ ፔንስልቬንያ	፭
	ሚያዝያ	ሀርመኒ፣ ፔንስልቬንያ	፮፣ ፯፣ ፰፣ ፱፣ ፲
	ግንቦት	ሀርመኒ፣ ፔንስልቬንያ	፲፩፣ ፲፪፣ ፲፫*
	ሰኔ	ፈየት፣ ኒው ዮርክ	፲፬፣ ፲፭፣ ፲፮፣ ፲፯፣ ፲፰
	በጋ	ማንችስተር፣ ኒው ዮርክ	፲፱
፲፰፻፹		ዌይን አውራጃ፣ ኒው ዮርክ	፳፩
	ሚያዝያ	ፈየት፣ ኒው ዮርክ	፳፪*፣ ፳፫
	ሚያዝያ	ማንችስተር፣ ኒው ዮርክ	፳፪፣ ፳፫
	ሐምሌ	ሀርመኒ፣ ፔንስልቬንያ	፳፬፣ ፳፭፣ ፳፮
	ነሐሴ	ሀርመኒ፣ ፔንስልቬንያ	፳፯
	መስከረም	ፈየት፣ ኒው ዮርክ	፳፰፣ ፳፱፣ ፴፣ ፴፩
	ጥቅምት	ማንችስተር፣ ኒው ዮርክ	፴፪
	ጥቅምት	ፈየት፣ ኒው ዮርክ	፴፫
	ህዳር	ፈየት፣ ኒው ዮርክ	፴፬
	ታሕሣሥ	ፈየት፣ ኒው ዮርክ	፴፭*፣ ፴፮*፣ ፴፯*
፲፰፻፹፩	ጥር	ፈየት፣ ኒው ዮርክ	፴፰፣ ፴፱፣ ፴
	የካቲት	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፴፩፣ ፴፪፣ ፴፫፣ ፴፬
	መጋቢት	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፴፭፣ ፴፮፣ ፴፯፣ ፴፰
	ግንቦት	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፴፱፣ ፵
	ግንቦት	ቶምሰን፣ ኦሃዮ	፵፩
	ሰኔ	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፵፪፣ ፵፫፣ ፵፭፣ ፵፮
	ሐምሌ	ጽዮን፣ ጃክሰን አውራጃ፣ ሚዙሪ	፵፯
	ነሐሴ	ጽዮን፣ ጃክሰን አውራጃ፣ ሚዙሪ	፵፰፣ ፵፱
	ነሀሴ	ኢንድፔንደንስ፣ ሚዙሪ	፶
	ነሀሴ	የምዙሪ ወንዝ፣ ሚዙሪ	፶፩
	ነሐሴ	ቻሪቶን፣ ሚዙሪ	፶፪
	ነሐሴ	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፶፫
	መስከረም	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፶፬
	ጥቅምት	ሐይረም፣ ኦሃዮ	፶፭፣ ፶፮
	ህዳር	ሐይረም፣ ኦሃዮ	፩፣ ፶፯፣ ፶፰፣ ፶፱፣ ፷፣ የ፴፫
	ታህሳስ	ሐይረም፣ ኦሃዮ	፷፩
	ታህሳስ	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፷፪
፲፰፻፹፪	ጥር	ሐይረም፣ ኦሃዮ	፷፫
	ጥር	ኦምኸርስት፣ ኦሃዮ	፷፭
	የካቲት	ሐይረም፣ ኦሃዮ	፷፮
	መጋቢት	ሐይረም፣ ኦሃዮ	፷፯፣ ፷፱፣ ፸፣ ፸፩

*በተጠቆመው ቦታ ላይ ወይም አቅራቢያ

ቀን (እ.አ.አ.)		ቦታ	ክፍሎች
	መጋቢት	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፫፯
	ሚያዝያ	ኢንድፔንደንስ፣ ሚዙሪ	፲፬፣ ፲፫
	ነሀሴ	ሐይረም፣ ኦሃዮ	፲፱
	መስከረም	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፲፰
	ህዳር	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፲፯
	ታህሳሥ	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፲፯፣ ፲፯*፣ ፲፯
፲፯፻፹፫	የካቲት	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፲፱
	መጋቢት	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፣ ፲፩፣ ፲፪
	ግንቦት	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፲፫
	ሰኔ	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፲፭፣ ፲፮
	ነሐሴ	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፲፰፣ ፲፯፣ ፲፯
	ጥቅምት	ፔሪስበርግ፣ ኒው ዮርክ	፣
	ታህሣሥ	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፣ ፲፩
፲፯፻፹፬	የካቲት	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፣ ፲፪፣ ፲፫
	ሚያዝያ	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፣ ፲፰*
	ሰኔ	ፊሺንግ ወንዝ፣ ሚዙሪ	፣ ፲፭
	ህዳር	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፣ ፲፮
፲፯፻፹፭	ሚያዝያ	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፣ ፲፯
	ነሐሴ	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፣ ፲፱፣ ፲፱
	ታህሳስ	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፣ ፲፯
፲፯፻፹፮	ጥር	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፣ ፲፱፣ ፲፯
	መጋቢት	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፣ ፲፱
	ሚያዝያ	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፣ ፲፣
	ነሃሴ	ሴለም፣ ማሳቹሴትስ	፣ ፲፣፩
፲፯፻፹፯	ሐምሌ	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፣ ፲፣፪
፲፯፻፹፰	መጋቢት	ፋር ዌስት፣ ሚዙሪ	፣ ፲፣፫*
	ሚያዝያ	ፋር ዌስት፣ ሚዙሪ	፣ ፲፣፩፣ ፲፣፭
	ግንቦት	ስፕሪንግ ሂል፣ ዴቪስ አውራጃ፣ ሚዙሪ	፣ ፲፣፯
	ሐምሌ	ፋር ዌስት፣ ሚዙሪ	፣ ፲፣፯፣ ፲፣፰፣ ፲፣፱፣ ፲፰
፲፯፻፹፱	መጋቢት	ልብርቲ እስር ቤት፣ ክለይ አውራጃ፣ ሚዙሪ	፣ ፲፰፩፣ ፲፰፪፣ ፲፰፫
፲፯፻፺፩	ጥር	ናቩ፣ ኢሊኖይ	፣ ፲፰፬
	መጋቢት	ናቩ፣ ኢሊኖይ	፣ ፲፰፭
	ሐምሌ	ናቩ፣ ኢሊኖይ	፣ ፲፰፯
፲፯፻፺፪	መስከረም	ናቩ፣ ኢሊኖይ	፣ ፲፰፯፣ ፲፰፰
፲፯፻፺፫	የካቲት	ናቩ፣ ኢሊኖይ	፣ ፲፰፱
	ሚያዝያ	ራመስ፣ ኢሊኖይ	፣ ፲፱
	ግንቦት	ራመስ፣ ኢሊኖይ	፣ ፲፱፩
	ሐምሌ	ናቩ፣ ኢሊኖይ	፣ ፲፱፪
፲፯፻፺፬	ሰኔ	ናቩ፣ ኢሊኖይ	፣ ፲፱፭
፲፯፻፺፯	ጥር	ዊንተር ኳርተርስ (የአሁኑ ነብራስካ)	፣ ፲፱፯
፲፯፻፺፯	ጥቅምት	ሶልት ሌክ ሲቲ፣ ዩታ	አስተዳደሪያዊ አዋጅ ፩
፲፱፻፲፯	ጥቅምት	ሶልት ሌክ ሲቲ፣ ዩታ	፣ ፲፱፯
፲፱፻፳፱	ሰኔ	ሶልት ሌክ ሲቲ፣ ዩታ	አስተዳደሪያዊ አዋጅ ፪

*በተጠቆመው ቦታ ላይ ወይም አቅራቢያ

ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች

ክፍል ፩

በሀዳር ፩፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.)፣ በሀይረም ኦሀዮ በቤተክርስቲያኗ ሽማግሌዎች ልዮ ጉባዔ ወቅት በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ አማካይነት የተሰጠ ራዕይ። ከዚህ ጊዜ ቀደም ብሎ ብዙ ራእዮች ከጌታ ተሰጥተው ነበር፣ እናም እነዚህ ራዕዮች በመጽሐፍ መልክ ተጠርዘው እንዲታተሙ በጉባኤው ውሳኔ ከተሰጠባቸው ዋነኛ ሐሳቦች መካከል አንዱ ነበር። ይህ ክፍል በዚህ ዘመን የተሰጡትን ትምህርቶች፣ ቃል ኪዳኖች፣ እና ትዛዛትን በተመለከተ የጌታን መግቢያ የያዘ ነው።

፩–፲፣ የማስጠንቀቂያው ድምጽ ለሁሉም ሰው ነው፤ ፡–፲፮፣ ክህደትና ክፋት ዳግም ምፅዓትን ይቀድማሉ፤ ፲፯–፳፫፣ ጆሴፍ ስሚዝ የጌታን እውነት እና ሀይል በምድር ዳግመኛ እንዲመልስ ተጠርቷል፤ ፳፬–፴፫፣ መፅሐፈ ሞርሞን መጥቷል እናም እውነተኛ ቤተክርስቲያን ተመስርታለች፤ ፴፬–፴፮፣ ሰላምም ከምድር ይወሰዳል፣ ፴፯–፴፱፣ እነዚህን ትዛዛት መርምሩ።

ከፍ ብሎ የሚኖረው እና [a]አይኖቹንም በሁሉም ሰዎች ላይ የሆነው፣ የእርሱ ድምፅ አቤቱ እናንት [b]የቤተክርስቲያኔ ሰዎች ሆይ አድምጡ ይላል፣ አዎን እውነት እላለሁ፥ እናንት በሩቅ ያላችሁ፣ በባህር ደሴቶች ላይ ያላችሁ [c]ስሙ፣ በአንድነትም አድምጡ።

፪ በእውነት የጌታ [d]ድምጽ ለሁሉም ሰው ነውና፣ እናም [e]ማንም አያመልጥም፤ እናም የማያይ አይንም ሆነ የማይሰማ ጆሮ፣ ወይም የማይጣስ [f]ልብ አይኖርም።

፫ እናም [g]አመጸኞች በብዙ ሐዘን ይወጋሉ፤ ኃጢአታቸውም በቤቶች አናት ላይ [h]ይነገራሉ፣ የሚስጥር ተግባሮቻውም ይገለጣሉ።

፬ እናም [i]በመጨረሻዎቹ ቀናት፣ እኔ በመረጥኳቸው ደቀመዛሙርቶቼ አንደበት፣ የማስጠንቀቂያው [j]ድምጽ ለሁሉም ህዝብ ይሆናል።

፭ እናም እነርሱም ወደፊት ይሄዳሉ፣ ማንም አያግዳቸውም፣ እኔ ጌታ አዝዣቸዋለሁና።

፮ እነሆ አቤቱ! የምድር ነዋሪዎች፣ ለእናንተ [k]እንዲያሳትሙት የሰጠዋችሁ ይህ የእኔ [l]ስልጣን፣ እንዲሁም የአገልጋዮቼ ስልጣን፣ እናም ለመፅሐፈ ትእዛዛቴ መቅድም ነው።

፯ ስለዚህ፣ [m]ፍሩ እናም ተንቀጥቀጡ፣ አቤቱ! እናንት ሕዝቦች ሆይ፣ እኔ ጌታ በእነርሱ ያወጅኩት [n]ይፈጸማልና።

፰ እናም እውነት እላችኋለሁ፣ ይህንን የምስራች ይዘው ወደ ምድር ነዋሪዎች የሚሄዱ፣ ለእነርሱ በምድርም ሆነ በሰማይ፣

፩ [a] ሀ ት. እና ቃ. ፴፰፡፪–፰። ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ።
[b] ለ ፫ ኔፊ ፳፯፡፣ ፫፣ ት. እና ቃ. ፳፡፩። ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን።
[c] ሐ ዘዳግ. ፴፪፡፩።
[d] ፪ ሀ ት. እና ቃ. ፻፴፫፡፲፯። ለ ፊልጵ. ፪፡፱–፲፩።
[e] ሐ ቅ.መ.መ. ልብ።
[f] ፫ ሀ ቅ.መ.መ. አመጽ። ለ ሉቃ. ፰፡፲፣ ፲፪፡፣ ፲፭፣ ፪ ኔፊ ፳፯፡፣ ፲፩፣ ሞር. ፭፡፰።
[g] ፬ ሀ ቅ.መ.መ. የመጨረሻ ቀናት፣ የኋለኛው ቀናት። ለ ሕዝ. ፣ ፲፯–፳፩፣ ት. እና ቃ. ፳፣ ፴፯። ቅ.መ.መ. ማስጠንቀቅ፣ ማስጠንቀቂያ፤ የሚስዮን ስራ።
[h] ፯ ሀ ት. እና ቃ. ፫፪፡፳፩። ለ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—ስልጣን።
[i] ፯ ሀ ዘዳግ. ፭፡፳፱፤ መክ. ፲፪፡፲፣። ለ ት. እና ቃ. ፩፡፴፰።

የማያምኑትን እና ᵇአመጸኞችን ᵃየማሰር ኃይል ተሰጥቷቸዋል፤

፱ አዎን፣ እውነት፣ የእግዚአብሔር ᵇቁጣ ᵃበክፉዎች ላይ ያለልክ የሚወርድበት ቀን እስከሚመጣ ድረስ እንዲያስሯቸው—

፲ ጌታ መጥቶ ለእያንዳንዱን ሰው ᵇእንደ የስራው ᵃመጠን ᶜእስኪመልስ እና ሁሉም ሰው ለባልንጀራው በሰፈረበት መጠን እስ ከሚሰፍርበት ᶜቀን ድረስ የማሰር ኃይል ተሰጥቷቸዋል።

፲፩ ስለዚህ የሚሰማ ሁሉ ይሰማ ዘንድ፣ የጌታ ድምጽ እስከ ምድር ዳርቻ ነው፥

፲፪ ለሚመጣው ተዘጋጁ ተዘጋጁ፤ ጌታ ተቃርቧልና፤

፲፫ እናም የጌታ ᵇቁጣ ተቀጣጥሏል፣ እናም ᵃሰይፉም በሰማይ ታጥቧል፣ እንዲ ሁም በምድር ነዋሪዎችም ላይ ይወርዳል።

፲፬ እናም የጌታ ᵇክንድ ይገለጣል፤ የጌ ታን ድምጽ ሆነ ያገልጋዮቹን ድምጽ ᵃከማ ይሰሙ፣ ለነቢያት እና ለኃዋሪያት ቃላት ᶜትኩረት ከማይሰጡ ሰዎች መካከል ᵈየሚ ገለጡበት ቀን ይመጣል፣

፲፭ ᵇከስርዓቴ ᵃእርቀዋል፣ እናም ᶜዘለአ ለማዊ ቃል ኪዳኔን ᵈአፍርሰዋልና፤

፲፮ ጽድቁን ለመመስረት ጌታን ᵇአይፈል ጉም፣ ነገር ግን ሁሉም ሰው ᵃበገዛ ᶜመን ገዱ፣ እናም ቁሳቁሱ የጣኦት በሆነው፣ ᵈአምሳያውም የአለም በሆነው፣ ᵉአርጅ ቶም ᶠበባቢሎን በሚጠፋው፣ እንዲሁም በምትወድቀው በታላቂቷ ባቢሎን እንደ አምላኩ ምስል ይጓዛል።

፲፯ ስለዚህም እኔ ጌታ በምድር ᵇነዎሪ ዎች ላይ የሚመጣውን መቅሰፍት በማ ወቁ፣ ጀሴፍ ስሚዝ ዳግማዊን ጠራሁት እናም ከሰማይም ተናገርኩት እንዲሁም ትእዛዛትን ሰጠሁት፤

፲፰ እናም ደግሞ ይህንን የምስራች ለአ ለም እንዲያውጁ፣ እናም ይህን ሁሉ ያደረ ኩትም በነቢያቶች የተጻፈው ይፈጸም ዘንድ ለሌሎችም ትእዛዛትን ሰጥቻለሁ—

፲፱ የአለም ᵇደካማ ነገሮች ወደፊትም ይወጣሉ ብርቱውን እና ጠንካራውን ይሰ ብራሉ፣ ሰው ባልጀራውን መምከር አይ ገባውም፣ በስጋ ክንድ ᵃመመካት አይኖ ርበትም—

፳ ነገር ግን እያንዳንዱ ሰው የአለም አዳኝ በሆነው በጌታ እግዚአብሔር ስም ᵇይናገር ዘንድ፤

፳፩ ደግሞም እምነትም በምድር ይበዛ ዘንድ፤

፳፪ ዘለአለማዊ ᵇቃልኪዳኔ ይመሰረት ዘንድ፤

፳፫ ᵇየወንጌሌ ሙላት ᵃበደካሞች እና በተራ ሰዎች አማካይነት በነገስታት እና በገ

፳ ᵇ ቅ.መ.መ. አመጽ።
ᵃ ቅ.መ.መ. ማተም፣ ማስተሳሰር።
፱ ᵇ ራዕ. ፲፱፡፲፭–፲፮፣ ፩ ኔፊ ፳፪፡፲–፲፯።
ᵃ ሞዛያ ፲፮፡፪፣ ጆስ.—ማቴ. ፩፡ ፴፩፣ ፶፭።
፲ ᵇ ምሳ. ፳፡፲፪፣ አልማ ፱፡ ፳፰፣ ፴፩፡፪–፫፣ ት. እና ቃ. ፮፡ ፴፫።
ᵃ ማቴ. ፯፡፪።
ᶜ ሕዝ. ፯፡፱፣ ት. እና ቃ. ፶፮፡ ፲፱። ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—ዳኛ።
ᵈ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
፲፫ ᵇ ት. እና ቃ. ፳፫፡ ፮።
ᵃ ሕዝ. ፳፩፡ ፫፣ ት. እና ቃ. ፴፭፡ ፲፩።
፲፬ ᵇ ኢሳ. ፶፫፡ ፩።
ᵃ ፪ ኔፊ ፱፡ ፴፩፣ ሞዛያ ፳፯፡ ፳፯።
ᶜ ት. እና ቃ. ፲፩፡ ፪።
ᵈ የሐዋ. ፫፡ ፳፫፣ አልማ ፯፡ ፳፣ ት. እና ቃ. ፶፡ ፳፡ ፶፯፡ ፫።
፲፭ ᵇ ቅ.መ.መ. ስነስርዓቶች።
ᵃ ኢያ. ፳፫፡ ፲፯፣ ኢሳ. ፳፬፡ ፳።
ᶜ ቅ.መ.መ. አዲስ እና የዘለአለም ቃል ኪዳን።
ᵈ ቅ.መ.መ. ክህደት።
፲፮ ᵇ ማቴ. ፮፡ ፴፫።
ᵃ ኢሳ. ፶፫፡ ፮።
ᶜ ት. እና ቃ. ፳፪፡ ፮።
ᵈ ዘፀአ. ፳፡ ፱፣ ፫ ኔፊ ፳፩፡ ፲፯። ቅ.መ.መ. ጣኦት አምላኪ።
ᵉ ኢሳ. ፶፡ ፱።
ᶠ ት. እና ቃ. ፳፭፡ ፳፩፣ ፲፡ ፳፭–፳፮፣ ፲፡ ፳ ቅ.መ.መ. ባቢሎን፤ አለማዊነት።
፲፯ ᵇ ኢሳ. ፳፭፡ ፩–፮።
፲፱ ᵇ የሐዋ. ፡ ፲፫፣ ፩ ቆሮ. ፩፡ ፳፯፣ ት. እና ቃ. ፴፭፡ ፲፫፣ ፲፡ ፳፭–፳፱። ቅ.መ.መ. ገር፣ ገርነት።
ᵃ ፪ ኔፊ ፳፰፡ ፴፩። ቅ.መ.መ. መታመን።
፳ ᵇ ቅ.መ.መ. መመስከር።
፳፩ ᵇ ት. እና ቃ. ፴፱፡ ፲፩። ቅ.መ.መ. ቃል ኪዳን፣ አዲስ እና የዘለአለም ቃል ኪዳን።
፳፫ ᵇ ቅ.መ.መ. ወንጌል።
ᵃ ፩ ቆሮ. ፩፡ ፳፯–፳፱።

ዝዎች ፊት እስከ ዓለም መጨረሻ ድረስ
ሐይታወጅ ዘንድ ተሰጥቷቸዋል።
፳፬ እነሆ፣ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፣ እኔም
ተናግሬዋለሁ፤ እነዚህ ሠትእዛዛት ከእኔ
ዘንድ ናቸው፣ በድክመታቸው፣ ሀእንደ
ቋንቋቸው ወደ ሐመረዳት ይመቱ ዘንድ ለአ
ገልጋዮቼ ተሰጥተዋቸዋል።
፳፭ እናም ስህተትን እስከፈጸሙ ድረስ
ስተታቸውን እንዲታወቁ፤
፳፮ እናም ለጥበብንም እስከፈለጉ ድረስ
ያንኑ ይማሩ ዘንድ፤
፳፯ እናም ኃጢአትን እስከሰሩ ድረስ
ለንስሀ እንዲገቡ ሀይገሰጹ ዘንድ፤
፳፰ ለትሁት እስከሆኑ ድረስ እንዲበረቱ
እና ከላይም እንዲባረኩ፣ እንዲሁም ከጊዜ
ወደ ጊዜ ሀእውቀትንም ይቀበሉ ዘንድ ነው።
፳፱ እና አገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማ
ዊም ቢሆን የኔፋውያንን መዝገብ ከተቀ
በለ በኋላ፤ አዎን በእግዚአብሔር ምህረት፣
በእግዚአብሔር ኃይል ለመፅሐፈ ሞርሞንን
የመተርጎም ኃይል ይኖረው ዘንድ ነው።
፴ እናም ደግሞ እነዚህ ትእዛዛት የተሰ
ጣቸው በምድር ገጽ ላይ ሁሉ ብቸኛ እው
ነተኛ እና ህያው የሆነችውን ለቤተክርስ
ቲያን፣ እኔም ጌታ በጣም ሀየተደሰትኩባ
ትን የእዚህችን ሐቤተክርስቲያን መሰረት
የመጣል፣ እና ለከጭለማ እና ከተደበቀች
በት የማውጣት ለኃይል ይኖራቸው ዘንድ
ነው። እነዚህን ነገሮች ለቤትክርስቲያኗ ስና
ገር በጋራ እንጂ በተናጠል አይደለም—
፴፩ እኔ ጌታ ለኃጢአትን በዝቅተኛ ደረጃ
መመልከት አይቻለኝምና፤
፴፪ ሆኖም፣ ንስሀ የሚገባ እና የጌታን
ትእዛዛት የሚጠብቅ ለይቅርታን ይቀበላል፤
፴፫ እናም ለንስሀ የማይገባ፣ የተቀበለ
ውም ብርሀን ቢሆን እንኳን ከእርሱ ሀይወ
ሰድበታል፤ ሐመንፈሴም ከሰው ጋር ዘወ
ትር ለአይሆንምና፣ ይላል የሰራዊት ጌታ።
፴፬ እናም ደግሞ፣ እውነት እላችኋለሁ፣
አቤቱ የምድር ነዋሪዎች ሆይ፥ እኔ ጌታ እነ
ዚህን ነገሮች ለስጋ ለባሽ ለሁሉ ለማሳወቅ
ፍቃደኛ ነኝ፤
፴፭ እኔም ለሰዎች ለአላደላም፣ እናም
ሀቀኑ በፍጥነት እንደመጣ ሁሉም ሰው ያው
ቀው ዘንድ ፍቃዴ ነው፤ ሐሰላም ከምድር
የሚወሰድበት፣ እና ለዲያብሎስም በግዛ
ቱም ላይ ኃይል የሚያገኝበት ሰዓት አል
ደረሰም ነገር ግን ተቃርቧል።
፴፮ እናም ደግሞ ጌታ ለበቅዱሳኑ ላይ
ኃይል ይኖረዋል፣ እናም ሀበመካከላቸውም
ሐይነግሳል እናም ለበኢዱሜአ ወይም በአ
ለም ላይ ለበፍርድ ይወርዳል።

፳፫ሐ ቅ.መ.መ. የሚስዮን ስራ።
፳፬ ለ ፪ ኔፊ ፴፫፡ ፲–፲፭፤
ሞሮኒ ፲፡ ፳፯–፳፰።
ለ ፪ ኔፊ ፴፭፡ ፫፤
ኤተር ፲፪፡ ፴፱።
ሐ ት. እና ቃ. ፱፡ ፲፪።
ቅ.መ.መ. ማስተዋል።
፳፭ ለ ያዕ. ፭፡ ፭፤
ት. እና ቃ. ፵፪፡ ፳፳።
ቅ.መ.መ. ጥበብ።
፳፮ ለ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣
ንስሀ መግባት።
ለ ቅ.መ.መ. መገሰጽ፣ ተግሳጽ።
፳፰ ለ ቅ.መ.መ. ትሁት፣ ትሕትና።
ለ ቅ.መ.መ. እውቀት።
፳፱ ለ ቅ.መ.መ. መፅሐፈ ሞርሞን።
፴ ለ ኤፌ. ፪፡ ፭፤ ፲፭–፲፡።
ቅ.መ.መ. የእውነተኛ
ቤተክርስቲያን ምልክቶች።
ለ ት. እና ቃ. ፴፳፡ ፲።
ሐ ቅ.መ.መ. የኋለኛው ቀን
ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ
ቤተክርስቲያን፣
የወንጌል ዳግም መመለስ።
መ ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ጭለማ።
ሠ ት. እና ቃ. ፭፡ ፱–
፭፡ ፲፯–፲፰።
፴፩ ለ አልማ ፴፭፡ ፲፯፤
ት. እና ቃ. ፳፡ ፱።
ቅ.መ.መ. ኃጢያት።
፴፪ ለ ት. እና ቃ. ፶፡ ፴፪–፴፫።
ቅ.መ.መ. ይቅርታ ማድረግ።
፴፫ ለ ሞዛያ ፳፯፡ ፴፪።
ለ አልማ ፳፱፡ ፴፣
ት. እና ቃ. ፳፡ ፪–፫።
ሐ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
መ ዘፍጥ. ፮፡ ፫፤
፪ ኔፊ ፳፮፡ ፲፭፤
ሞር. ፭፡ ፲፯፤
ኤተር ፪፡ ፲፭፤
ሞሮኒ ፱፡ ፡
ሠ ማቴ. ፳፡ ፲፱፤
ት. እና ቃ. ፭፡ ፪፤ ፶፪፡ ፶፫።
፴፭ ለ ዘዳግ. ፲፡ ፲፯፤
የሐዋ. ፲፡ ፡፡
ሞሮኒ ፳፡ ፲፪፤
ት. እና ቃ. ፡፡ ፲፯፤
ለ ቅ.መ.መ. የመጨረሻ
ቀናት፣ የኋለኛው ቀናት።
ሐ ት. እና ቃ. ፲፲፡ ፭–፪።
ቅ.መ.መ. ሰላም፣
የጊዜዎች ምልክቶች።
መ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
፴፮ ለ ቅ.መ.መ. ቅዱሳን።
ለ ዘካ. ፪፡ ፲–፲፭፤
ት. እና ቃ. ፳፱፡ ፲፭፤
፲፲፡ ፲፣ ፲፯–፲፱።
ሐ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ
ክርስቶስ—የክርስቶስ
የአንድ ሺህ አመት ግዛት።
መ ቅ.መ.መ. አለም።
ሠ ቅ.መ.መ. ዳኛ፣ ፍርድ።

፴፯ እነዚህን ᵇትእዛዛት መርምሩ፣ የታ
መኑና እውነተኛዎች ናቸውና፣ እናም
በውስጣቸው ያሉት ትንቢቶች እና ᵃየተ
ስፋ ቃላት ሁሉ ይፈጸማሉ።
፴፰ እኔ ጌታ የተናገርኩትን፣ ተናግሬያ
ለሁ፣ እናም አላመካኝም፤ ሰማያትና ምድር
ቢያልፉም ᵇቃሌ ግን አያልፍም፣ ነገር ግን
ሁሉም ᵃይፈጸማል፣ በእኔ ᶜድምጽ ሆነ
ᵐበአገልጋዮቼ ድምጽ፣ ያም ᵐእንድ ነው።
፴፱ ስለሆነም፣ እናም አስተውሉ፣ ጌታ
አምላክ ነው፣ ᵇመንፈስም ይመሰክራል፣
እናም ምስክርነቱም እውነት ነው፣ እናም
ᵃእውነት ከዘለአለም እስከ ዘለአለም ይኖ
ራል። አሜን።

ክፍል ፪

በመስከረም ፳፩፣ ፲፰፻፳፰ (እ.አ.አ.) ምሽት በማንችስተር፣ ኒው ዮርክ በነቢዩ አባት ቤት ውስጥ ከመልአኩ ሞሮኒ ለጆሴፍ ስሚዝ ከተሰጡ ቃላት ከጆሴፍ ስሚዝ ታሪክ ውስጥ የተውጣጣ ምንባብ። በአሁኑ ወቅት መፅሐፈ ሞርሞን በመ ባል በአለም ፊት ያለውን ጽሁፍ ከጻፉት ረጅም የታሪክ ጸሀፊያን ሀረግ ሞሮናይ የመጨረሻው ነበር (ሚልኪያስ ፬፡ ፭–፮፤ እንዲሁም ክፍሎች ፳፯፡ ፱፤ ፲፫፡ ፲፮፤ እና ፲፳፯፡ ፲፰ን አነጻጽሩ።)

፩፣ ኤሊያስ ክህነትን ይገልጣል፤ ፪–፫፣ የአባቶች የተስፋ ቃል በልጆች ልብ ይተ ከላል።

፩ እነሆ ᵇታላቁና የሚያስፈራው የጌታ ቀን ከመምጣቱ በፊት በነቢዩ ᵃኤሊያስ እጅ ክህ ነትን እገልጥላችኋለው።
፪ እናም ለአባቶች የተገባውን ᵇየተስፋ ቃል በልጆች ልብ ᵃይተክላል፣ እናም የል ጆቹም ልብ ወደ አባቶቻቸው ይመለሳል።
፫ እንዲህ ባይሆን ኖሮ፣ መላው ምድር በምጽአቱ በጠፋ ነበር።

ክፍል ፫

ሐምሌ ፲፰፻፳፰ (እ.አ.አ.) በሀርመኒ ፔንስልቬንያ ውስጥ መፅሐፈ ሌሒ ተብሎ ይጠራ የነበረውን የተተረጎመበት ፳፲፮ የመፅሐፈ ሞርሞን ገጾች የመጀመሪያ ክፍል መጥፋት በተመለከተ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተሰጠ ራዕይ። ነቢዩ በቸልተኛነት እነዚህን ገጾች ለጥቂት ጊዜ የመፅሐፈ ሞርሞን ትርጉም ጸሐፊ በመሆን ያገለግል

፴፯ ᵇ ቅ.መ.መ. ቅዱሳት
መጻህፍት።
ᵃ ት. እና ቃ. ፶፰፡ ፴፩፤
፳፪፡ ፮፤ ፹፪፡ ፲።
፴፰ ᵇ ፪ ነገሥ. ፲፡ ፲፣
ማቴ. ፭፡ ፲፰፡ ፳፬፡ ፴፩፤
፪ ኔፊ ፱፡ ፲፮፤
ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፡ ፴፭።
ᵃ ት. እና ቃ. ፲፩፡ ፳፬።
ᶜ ዘዳግ. ፲፰፡ ፲፰፣
ት. እና ቃ. ፲፰፡ ፴፫–፴፰፣
፳፩፡ ፭።
ᵈ ቅ.መ.መ. ራዕይ፤
ድምፅ።
ᵉ ቅ.መ.መ. ነቢይ።
ᶠ ቅ.መ.መ. ስልጣን፤
የቤተክርስቲያን
መሪዎችን መደገፍ።
፴፱ ᵇ ፩ ዮሐ. ፭፡ ፮፤
ት. እና ቃ. ፳፡ ፳፯፤
፶፪፡ ፲፯።
ᵃ ቅ.መ.መ. እውነት።
፪ ፩ ᵇ ት. እና ቃ. ፴፪፡ ፮–
፱፤ ፶፫፡ ፲፯–፳፯።
ᵃ ሚል. ፬፡ ፭–፮፤
፫ ኔፊ ፳፭፡ ፭–፮፤
ት. እና ቃ. ፲፣ ፲፫–፲፭፤
፲፳፡ ፲፯፤
ጆ.ስ.—ታ. ፩፡ ፴፰–፴፱።
ᵇ ቅ.መ.መ. ኤልያስ፣
የክህነት ቁልፎች።
፪ ᵇ ቅ.መ.መ. ለሙታን
ደህንነት፤
ማተም፣ ማስተሳሰር።
ᵃ ት. እና ቃ. ፳፯፡ ፱፤
፶፰፡ ፲፯–፲፯።

ለነበረው ማርቲን ሀሪስ አሳልፎ ሰጠ። ራዕዩ በኡሪምና ቱሚም አማካይነት የተሰጠ ነው። (ክፍል ፲ን ተመልክቱ።)

፩–፬፣ የጌታ ጎዳና አንድ እና ዘለአለማዊ ዙሪያ ነው፤ ፭–፲፭፣ ጆሴፍ ስሚዝ ንስሀ መግባት ወይም የመተርጎም ስጦታውን ማጣት አለበት፤ ፲፮–፳፣ መፅሐፈ ሞር ሞን የሌሒ ዘሮችን ለማዳን ይመጣል።

፩ የእግዚአብሔር [a]ስራ፤ ጥበብ፤ እና ዓላማ ሊከሸፍም ሆነ ከንቱ ሊሆን አይች ልም።

፪ [b]እግዚአብሔር በተጣመመ መንገድ አይጓዝም፣ ወደ ቀኝ ወይም ወደ ግራ አይ ዞርም፣ የተናገረውንም አይለውጥም፣ ስለ ዚህ መንገዱ ቀጥተኛ ነው፣ [c]ጎዳናውም አንድ እና ዘለአለማዊ ዙሪያ ነው።

፫ አስታውሱ፣ አስታውሱ የሚሰናከለው የሰው ስራ እንጂ የእግዚአብሔር [d]ስራ አይ ደለም፤

፬ ሰው ብዙ ራዕይ ቢቀበል፣ እናም ብዙ ታላላቅ ነገሮችን ለመስራት ሀይል ቢኖረ ውም፣ ነገር ግን በራሱ ጥንካሬ [e]ቢታበይ፣ የእግዚአብሔርን [f]ምክር ከንቱ ቢያደርግ እናም [g]በስጋው እና በራሱ ፈቃድ ቢመራ፣ ውድቀትንና የእግዚአብሔርን [h]መቀል በራሱ ላይ ማምጣት አለበት።

፭ እነሆ፣ እነዚህ ነገሮች ተሰጥተውሀል፣ ነገር ግን የተሰጡህ ትእዛዛቶች እንዴት የጠ በቁ ነበሩ፤ እናም ካልተላለፍካቸው፣ ለአ ንተ የተገባልህን የተሰሩ ቃላት እንዲሁ አስ ታውስ።

፮ እናም እነሆ፣ ምን ያህል ጊዜ የእግዚአ ብሔርን ትእዛዛትና ህግጋት [i]ተላልፈሀል፤ እናም በሰዎችም [j]ሀሳብ ምን ያህል ሄደሀል።

፯ ስለሆነም እነሆ ሰውን ከእግዚአብ ሔር አስበልጠህ [k]ፍርሀት አልነበረብህም። ምንም እንኳን ሰዎች የእግዚአብሔርን ምክር ከንቱ ቢያደርጉም እናም ቃሉንም [l]ቢንቁ—

፰ ነገር ግን ታማኝ መሆን ነበረብህ፤ እናም እጁን ዘርግቶ [m]ከጠላትም ክፉ [n]ፍላፃ ይደ ግፍህ ነበር፤ እናም [o]በመከራህ ጊዜ ሁሉ ከአንተ ጋር ይገኝ በነበር።

፱ እነሆ አንተ ጆሴፍ ነህ፣ እናም የጌታን ስራ እንድትሰራ ተመርጠሀል፣ ነገር ግን በመተላለፍህ ምክንያት ካልተጠነቀቅህ ትወድቃለህ።

፲ ነገር ግን አስታውስ፤ እግዚአብሔር መሀሪ ነው፤ ከሰጠሁህ ትእዛዛት ተጻራሪ የሆነውን ለሰራህበት ንስሐ ግባ፣ እናም አሁን የተመረጥህ ነህ፣ እናም ለስራው ዳግም ተጠርተሀል፤

፲፩ ይህን ካላደረግህ በቀር፣ ትተዋለህ እናም እንደሌሎችም ሰዎች ትሆናለህ፣ እና ስጦታም አይኖርህም።

፲፪ እናም እግዚአብሔር የሰጥህን [p]የመ ተርጎም መንፈሣዊ ብርሀንና ሀይል አሳል ፈህ በሰጠህ ጊዜ፣ የተቀደሰውን ነገር በኃ ጢአተኛ [q]ሰው እጅ ውስጥ እንዲገባ አሳ ልፈህ ሰጥተሀል፣

---

[a] ፩ ሀ መዝ. ፰፡፲–፱፤
ት. እና ቃ. ፲፡ ፶፫።
[b] ፪ ሀ አልማ ፯፡ ፳።
ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣
አምላክ።
ለ ፩ ኔፊ ፲፡ ፲፰–፲፱፤
ት. እና ቃ. ፴፭፡ ፩።
[c] ፫ ሀ የሐዋ. ፭፡ ፴፰–፴፱፤
ሞር. ፰፡ ፳፪፤
ት. እና ቃ. ፲፡ ፶፫።
[d] ፬ ሀ ት. እና ቃ. ፲፡ ፶፫–፶፮፤
ቅ.መ.መ. ኩራት።
ለ ያዕቆ. ፬፡ ፲፤
አልማ ፴፯፡ ፴፯።
ቅ.መ.መ. ምክር (ስም)፤
የእግዚአብሔር ትእዛዛት።
ሐ ቅ.መ.መ. ስጋዊ።
መ ቅ.መ.መ. በቀል።
[e] ፮ ሀ ት. እና ቃ. ፭፡ ፳፭፤
ጆ.ስ.—ታ. ፩፡ ፳፰–፳፱።
ለ ት. እና ቃ. ፶፭፡ ፳፱፤
፶፮፡ ፯።
[f] ፯ ሀ መዝ. ፳፯፡ ፩፤
ሉቃ. ፱፡ ፳፯፤
ት. እና ቃ. ፻፳፪፡ ፱።
ቅ.መ.መ. መበርታት፣
ብርቱነት፤
ፍርሀት።
ለ ዘሌዋ. ፳፮፡ ፴፪–፴፫፤
፩ ኔፊ ፲፱፡ ፯፤
ያዕቆ. ፪፡ ፳–፲።
[g] ፰ ሀ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
ለ ኤፌ. ፮፡ ፲፮፤
፩ ኔፊ ፲፭፡ ፳፬፤
ት. እና ቃ. ፳፯፡ ፲፯።
ሐ አልማ ፴፰፡ ፭።
[h] ፲፪ ሀ ት. እና ቃ. ፩፡ ፳፱፤ ፭፡ ፬።
ለ ት. እና ቃ. ፲፡ ፮–፰።

፲፫ የእግዚአብሔርንም ምክር ከንቱ ላደ
ረገ ሰው፣ እና በእግዚአብሔር ፊት የተ
ደረገውን በጣም የተቀደሱ ቃል ኪዳኖ
ችን ላፈረሰና፣ በራሱ ፍርድ ላይ ለሚመ
ካና በራሱም ጥበብ [ሀ]ለሚታበይ ሰው አሳ
ልፈህ ሰጥተሀል።

፲፬ እናም በዚህ መክንያት ነው ለጊዜው
ስጦታህን ያጣኸው—

፲፭ ምክንያቱም [ለ]የመሪህን ምክር ከመጀ
መሪያው ጀምሮ እንዲረገጥ አድርገኃልና።

፲፮ ሆኖም፣ ስራዬ ወደፊት ይቀጥላል፣
[ሐ]የአዳኝ እውቀት ወደ አለም በአይሁዶች
[መ]ምስክርነት እንደመጣ እንዲሁ፣ የአዳኝ
[ሠ]እውቀት ወደ ህዝቤ ይመጣል—

፲፯ እንዲሁም [ረ]ለኔፋውያን፣ እናም ለያ
ዕቆባውያን እናም ለዮሴፋውያን እናም
ለዞራማውያን በአባቶቻቸው ምስክርነት
ይመጣል—

፲፰ እናም ይህ [ሰ]ምስክርነት በአባቶቻቸው
ክፋት ምክንያት እምነት በማጣት [ሸ]ወደ
መነመኑት፣ ጌታ ወንድሞቻቸው ኔፋው
ያንን፣ በኃጢአታቸው እና በእርኩሰነታ
ቸው የተነሳ፣ [ቀ]እንዲጠፉ ወዳደረጋቸው፣
ወደ [በ]ላማናውያን እና ልሙኤላውያን እና
እስማኤላውያን እውቀት ይመጣል።

፲፱ በዚህ [ተ]ዓላማ ምክንያት ነው ጽሁፎቼን
የያዘው ይህ [ቸ]ሰሌዳ የተጠበቀው—ጌታ ለህ
ዝቦቹ የገባው [ኀ]የተስፋ ቃል ይፈጸም ዘንድ፣

፳ እናም [ነ]ላማናውያን ወደ አባቶቻቸው
እውቀት ይመጡ ዘንድ፣ እናም የጌታን የተ
ስፋ ቃል ያውቁ ዘንድ፣ እናም ወንጌልንም
[አ]ያምኑ ዘንድ፣ እናም በኢየሱስ ክርስቶስ
መልካም ስራ [ኀ]ይመኩ ዘንድ፣ እናም በእ
ምነት በስሙ [መ]ይከብሩ ዘንድ፣ እናም በን
ሰሀቸው ይድኑ ዘንድ ነው ሰሌዳው የተጠ
በቀው። አሜን።

ክፍል ፴

የካቲት ፲፰፻፳፱ (እ.አ.አ.) በሀርመኒ ፔንስልቬንያ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል ለአባቱ ለጆሴፍ ስሚዝ ቀዳማዊ የተሰጠ ራዕይ።

፩–፬፣ የጌታን አገልጋዮች የጀግና አገልግ ሎት ያድናቸዋል፤ ፭–፯፣ አምላካዊ ባህሪ ያት ላገልግሎቱ ብቁ ያደርጋቸዋል፤ ፰፣ የእግዚአብሔር ነገሮች መሻት አለባቸው።

፩ አሁን እነሆ፣ በሰዎች ልጆች መካከል [ሀ]ድንቅ ስራ ሊመጣ ነው።

፪ ስለዚህ እናንት በእግዚአብሔር [ለ]አገል ግሎት ውስጥ መሳተፍ የጀመራችሁ፤ በመ ጨረሻው ቀን በእግዚአብሔር ፊት [ሐ]ያለ ወቀሳ ትቆሙ ዘንድ፣ በሙሉ [መ]ልባችሁ፤ ኃይላችሁ፣ አዕምሮአችሁ እና ጉልበታችሁ [ሠ]እንደምታገለግሉት አረጋግጡ።

፫ ስለዚህ፣ እግዚአብሔርን ለማገልገል

፲፫ *ሀ* ቅ.መ.መ. ኩራት።
፲፭ *ለ* ይህም ጌታ ማለት ነው።
፲፮ *ሀ* ቅ.መ.መ. አዳኝ።
ለ ፩ ኔፊ ፲፫፡፳፫–፳፭፤
፪ ኔፊ ፳፱፡፱–፲፤
ሐ ሞዛያ ፫፡፳።
፲፯ *ሀ* ፪ ኔፊ ፭፡፳–፴።
፲፰ *ሀ* ቅ.መ.መ. መፅሐፈ ሞርሞን።
ለ ፪ ኔፊ ፳፯፡፲፭–፲፯።
ሐ ሞር. ፳፡፪–፫።
መ ፪ ኔፊ ፭፡፲፬፤
ኢኖስ ፩፡፲፫–፲፰።
፲፱ *ሀ* ፩ ኔፊ ፱፡፫፤ ፭።
ለ ቅ.መ.መ. የወርቅ ሰሌዳዎች።
ሐ ፫ ኔፊ ፭፡፲፬–፲፭፤
ት. እና ቃ. ፲፡፵፯–፶።
፳ *ሀ* ፪ ኔፊ ፴፡፫–፭፤
ት. እና ቃ. ፳፰፡፳፡፳፤
፵፱፡፳፬፡፴፪።
ለ ሞር. ፫፡፲፱–፳፩።
ሐ ፪ ኔፊ ፴፩፡፲፱፤
ሞሮኒ ፯፡፡፡፡
መ ሞሮኒ ፯፡፳፯፤ ፴፳።
፴ ፩ *ሀ* ኢሳ. ፳፱፡፲፡፡
፩ ኔፊ ፲፡፯፤ ፳፪፡፳፤
ት. እና ቃ. ፯፡፩፤ ፲፳፡፵፬፡፡
ቅ.መ.መ. የወንጌል
ዳግም መመለስ።
፪ *ሀ* ቅ.መ.መ. አገልግሎት።
ለ ፩ ቆሮ. ፩፡፳፤
ያዕቆ. ፩፡፲፱፤
፫ ኔፊ ፳፯፡፳።
ሐ ቅ.መ.መ. ልብ፤
አዕምሮ።
መ ኢያ. ፳፪፡፩፤
፩ ሳሙ. ፯፡፫፤
ት. እና ቃ. ፳፡፲፱፤ ፷፯፡፩።

ፈቃድ ካላችሁ ወደስራው [ሀ]ተጠርታችኋል፤

፬ ስለሆነም እነሆ [ሀ]እርሻው ነጥቷል [ለ]አዝመራውም ዝግጁ ነው፤ እናም እስተውሉ፣ በጥንካሬው የሚያጭድ እንዳይጠፋ ዘንድ [ሐ]በጎተራው ይከምራል፣ ነገር ግን ለነፍሱ ደህንነትን ያመጣል፤

፭ እናም [ሀ]እምነት፣ [ለ]ተስፋ፣ [ሐ]ለጋስነትና [መ]ፍቅር፣ ሙሉ [ሠ]አይኑን ወደ እግዚአብሔር [ረ]ክብር ከማድረግ ጋር ለስራ ብቁ ያደርጉታል።

፮ እምነት፣ [ሀ]ምግባረ በጎነት፣ ዕውቀት፣ ራስን መግዛት፣ [ለ]ትዕግስት፣ ወንድማዊ ደግነት፣ አምላካዊነት፣ ልግስና፣ [ሐ]ትህትና፣ [መ]ትጋትን አስታውሱ።

፯ [ሀ]ለምኑ፣ እናም ይሰጣችኋል፤ አንኳኩ፣ ይከፈትላችኋል። አሜን።

ክፍል ፭

መጋቢት ፲፰፻፳፱ (እ.አ.አ.) በሀርመኒ፣ ፔንስልቬንያ፣ በማርቲን ሀሪስ ጥያቄ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ።

፩–፲፣ ይህ ትውልድ የጌታን ቃል በጆሴፍ ስሚዝ በኩል ይቀበላል፤ ፲፩–፲፰፣ ሶስቱ ምስክሮች ስለ መፅሐፈ ሞርሞን ይመሰክራሉ፤ ፲፱–፳፣ እንደ ቀድሞው ጊዜ የጌታ ቃል ይረጋገጣል፤ ፳፩–፴፭፣ ማርቲን ሀሪስ ንስሀ ይግባና ከምስክሮቹ አንዱ ይሁን።

፩ እነሆ፣ እንዲህ እልሀለሁ፣ አንተ አገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ፣ ዳግማዊ፣ ምስክርነትህን የሰጠህባቸውን [ሀ]ሰሌዳዎችን ከእኔ እንደተቀበልህ አገልጋዬ [ለ]ማርቲን ሀሪስ ከእኔ ምስክርነትን ፈልጓል፤

፪ እናም አሁን፣ እነሆ፣ ለእርሱም እንዲህ ትለዋለህ—ለአንተ የተናገረህ፣ እንዲህ ብሎሀል፥ እኔ ጌታ አምላክ ነኝ፣ እናም እነዚህን ነገሮች ለአንተ፣ ለአገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ፣ ዳግማዊ፣ ሰጥቻለሁ፣ እናም ለእነዚህም ነገሮች [ሀ]ምስክር ሆነህ እንድትቆም አዝዤሀለሁ፤

፫ እናም እኔ ላዘዝኩህ [ሀ]ሰዎች ካልሆነ በስተቀር እንዳታሳያቸው ከእኔ ጋር ቃል ኪዳን እንድትገባ አድርጌሀለሁ፤ በእነርሱም ላይ እኔ ካልሰጠሁህ በስተቀር ምንም አይነት [ለ]ስልጣን የለህም።

፬ እናም ሰሌዳዎቹን የመተርጎም ስጦታ አለህ፤ እናም ይህም በአንተ ላይ ካደረኩት የመጀመሪያው ስጦታ ነው፤ በዚህ አላማዬ እስኪሟላ ድረስ ሌላ ስጦታ እንዳለው እንዳታስመስል አዝዤሀለሁ፤ ይህም እስኪያልቅ ድረስ ሌላ ምንም ስጦታ አልሰጥህምና።

፭ እውነት፣ እልሀለው፣ ቃላቴን [ሀ]የማያ

፫ ሀ ት. እና ቃ. ፲፩፥፬፣ ፲፭፤ ፴፮፥፭፤ ፳፫፥፶፮።
ቅ.መ.መ. ጥሪ፣ በእግዚአብሔር መጠራት፣ የተጠራበት።
፬ ሀ ዮሐ. ፬፥፴፭፤ አልማ ፳፮፥፫–፭፤ ት. እና ቃ. ፲፩፥፫፤ ፴፫፥፫፣ ፯።
ለ ቅ.መ.መ. መከር።
ሐ ፩ ጢሞ. ፮፥፲፱።
፭ ሀ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
ለ ቅ.መ.መ. ተስፋ።
ሐ ቅ.መ.መ. ልግስና።
መ ቅ.መ.መ. ፍቅር።
ሠ መዝ. ፻፵፩፥፰፤ ማቴ. ፮፥፳፪፤ ሞር. ፰፥፲፭።
ረ ቅ.መ.መ. ክብር።
፮ ሀ ቅ.መ.መ. በጎነት።
ለ ቅ.መ.መ. ትዕግስት።
ሐ ቅ.መ.መ. ትሁት፣ ትሕትና።
መ ቅ.መ.መ. ትጋት።
፯ ሀ ማቴ. ፯፥፯–፰፤ ፪ ኔፊ ፴፪፥፬።
ቅ.መ.መ. ጸሎት።
፭ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. የወርቅ ሰሌዳዎች።
ለ ት. እና ቃ. ፭፥፳፫–፴፬፤ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፷፩።
፪ ሀ ቅ.መ.መ. ምስክር።
፫ ሀ ፪ ኔፊ ፳፯፥፲፫። ደግሞም “የሶስቱ ምስክሮች ምስክርነት”ን እና “የስምንቱ ምስክሮች ምስክርነት”ን በመፅሐፈ ሞርሞን የመጀመሪያ ገጾች ውስጥ እመልከቱ።
ለ ፪ ኔፊ ፫፥፲፩።
፭ ሀ ኤር. ፳፮፥፬–፭፤ አልማ ፭፥፵፯–፵፰፤ ት. እና ቃ. ፩፥፲፬።

ደምጡ ከሆነ በምድር ነዋሪዎች ላይ ዋይታ ይመጣል፤

፲፮ ስለዚህ ከአሁን በኋላ ᵐትሾማለህና ሂድ እናም ᵃቃሌን ለሰዎች ልጆች አድርስ።

፲፯ እነሆ፤ ቃላቴን ᵐየማያምኑ ከሆን፤ አገልጋዬ ጆሴፍ፣ የሚቻል ሆኖ ለአንተ የሰጠሁትን ነገሮች ሁሉ ብታሳያቸውም፣ አንተን አያምኑህም።

፲፰ አቤቱ፣ ይህ ᵐየማያምን ᵃአንገተ ደንዳና ትውልድ—ቁጣዬ በእነርሱ ላይ ተቀጣጥሏል።

፲፱ እነሆ፣ እውነት እልሀለሁ፣ አገልጋዬ ጆሴፍ፣ ለአንተ በአደራ የሰጠሁህን እነዚህን ነገሮች ᵐየጠበኩት በጥበብ አላማዬ ምክንያት ነው፣ እና ይህም ወደፊት ለሚመጡት ትውልዶች እንዲታወቅ ይደረጋል፤

፲ ነገር ግን ይህ ትውልድ በአንተ አማካይነት ቃሌን ያገኛል፤

፲፩ እናም ከአንተ ምስክርነት በተጨማሪ ጠርቼም የምሾማቸው፣ እነዚህንም ነገሮች የማሳያቸው የሶስቱ አገልጋዬቼ ᵐምስክርነት እናም በአንተ አማካይነት የተሰጡትን ቃሎቼን ይዘው ወደፊት ይጓዛሉ።

፲፪ አዎን፣ እነዚህ ነገሮች በእርግጥም እውነት እንደሆኑ ያውቃሉ፣ ምክንያቱም ከሰማይ እኔ አውጅላቸዋለሁና።

፲፫ እነዚህን ነገሮች እንዳሉ እና ማየት ይችሉ ዘንድ ሀይልን እሰጣቸዋለሁ፤

፲፬ እናም ᵐእንደጨረቃ የጠራች፣ እንደ ጸሀይ መልከ መልካም፣ ሰንደቅ ዓርማን እንዳነገበ ወታደር የምታስፈራው ᵃቤተ ክርስቲያኔ ከምድረበዳ በምትነሳበት እና መምጣት በምትጀምርበት ጊዜ፣ ይህን አይነት ምስክርነት፣ ይህን ሀይል፣ በዚህ ትውልድ መካከል እንዲቀበል ለሌላ ᵐለማንም አልሰጥም።

፲፭ እናም ስለቃሌ የሶስቱን ᵐምስክሮችን ምስክርነት እልካለሁ።

፲፮ እናም እነሆ፣ ቃሌን ᵐየሚያምኑ ሁሉ ᵃበመንፈሴ ᵐመገለጥ ᵐእጎበኛቸዋለሁ፤ እናም ከእኔ፣ እንዲሁም ከውሀ እና ከመንፈስ ᵐይወለዳሉ—

፲፯ እናም ገና ᵐስላልተሾማችሁ ለትንሽ ጊዜ መቆየት አለባችሁ—

፲፰ እናም በእነርሱ ላይ ልባቸውን ካደነደኑ ምስክርነታቸውም ይህንን ትውልድ ᵐይኮንን ዘንድ ይሄዳል፤

፲፱ በምድር ነዋሪዎች መካከል ᵐጥፋትና መከራ ይመጣል፣ ᵃንስሀ ካልገቡም ምድር ᵐባዶ እስክትሆን ድረስ ከጊዜ ወደ ጊዜ መውረዱ ይቀጥላል፣ እንዲሁም የምድር ነዋሪዎች ᵐበምዕዓቴም ብርሀን ይበላሉ እናም ፈጽሞ ይጠፋሉ።

፳ እነሆ፣ በኢየሩሳሌም መጥፊያ ጊዜ ᵐእንደነገርኳቸው ህዝብ፣ እነዚህን ነገሮች እነግርሀለሁ፤ በዚያም ጊዜ ᵃቃሌ እንደ ተረጋገጠ ሁሉ በዚህም ጊዜ ይረጋገጣል።

፳፩ እናም አሁን አገልጋዬ ጆሴፍ በፊቴ

፮ ሀ ት. እና ቃ. ፳፡፪–፫።
ቅ.መ.መ. መሾም፣ ሹመት።
ለ ፪ ኔፊ ፳፱፡፯።
፯ ሀ ሉቃ. ፲፯፡፳፯–፴፩፤ ት. እና ቃ. ፳፫፡፯–፲፪።
፰ ሀ ቅ.መ.መ. አለማመን።
ለ ሞር. ፰፡፴፫። ቅ.መ.መ. ኩራት።
፱ ሀ አልማ ፴፯፡፲፰።
፲፩ ሀ ፪ ኔፊ ፳፯፡፲፪፤ ኤተር ፭፡፫–፱፤ ት. እና ቃ. ፲፯፡፩–፫።
፲፩ ሀ ት. እና ቃ. ፲፭፡፴፩፤ ፲፱፡፫–፲፱።
ለ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን፤ የወንጌል ዳግም መመለስ።
ሐ ፪ ኔፊ ፳፯፡፲፫።
፲፫ ሀ ት. እና ቃ. ፲፯።
ቅ.መ.መ. የመፅሐፈ ሞርሞን ምስክሮች።
፲፮ ሀ ኤተር ፭፡፲፩።
ለ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
ሐ ት. እና ቃ. ፳፡፩–፫።
መ ፩ ኔፊ ፪፡፲፮።
ሠ ቅ.መ.መ. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ፤ ዳግመኛ መወለድን፣ ከእግዚአብሔር መወለድ፤ ጥምቀት፣ መጥመቅ።
፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. መሾም፣ ሹመት፤ ስልጣን።
፲፰ ሀ ፩ ኔፊ ፲፡፭፤ ፯፤ ት. እና ቃ. ፳፡፲፫–፲፭።
፲፱ ሀ ት. እና ቃ. ፳፱፡፲፤ ፴፭፡፲፤ ፴፫፡፲–፳፯።
ቅ.መ.መ. የመጨረሻ ቀናት፣ የኋለኛው ቀናት፤ የጊዜዎች ምልክቶች።
ለ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣ ንስሀ መግባት።
ሐ ኢሳ. ፳፱፡፩፤ ፭–፮።
መ ኢሳ. ፳፯፡፲፭–፲፯፤ ት. እና ቃ. ፱፴፫፡፴፩። ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
፳ ሀ ፩ ኔፊ ፩፡፲፳፤ ፪ ኔፊ ፳፭፡፱። ለ ት. እና ቃ. ፩፡፴፯።

በቅንነት እንድትራመድ፣ ንሰሀ እንድት ግባ፣ እናም ከዚህ በኋላ በሰዎች ሀሳብ እን ዳትወሰድ አዝሀለሁ፤

፳፪ እናም ያዘዝኩህ ትእዛዛት ᵐበመጠበቅ ጠንካራ እንድትሆን አዝሀለሁ፤ እናም ይህ ንን ካላደረግህ ᵃብትገደልም እንኳን ዘለአ ለማዊ ህይወትን እሰጥሀለሁ።

፳፫ እናም አሁን፣ ዳግም፣ አገልጋዬ ጆሴፍ፣ ምስክርነትን ስለሚፈልገው ᵐሰው እናገርሀለሁ—

፳፬ እነሆ እንዲህ እለዋለሁ፣ ራሱን ከፍ ከፍ ያደርጋል እና እራሱን በብቃት በፊቴ ዝቅ አያደርግም፤ ነገር ግን እራሱን በታላቅ ጸሎት እና እምነት ከልብ በሆነ ፈቃድ ዝቅ የሚያደርግ ከሆነ ማየት የሚሻውን ነገሮች ᵐእይታ አሰጠዋለሁ።

፳፭ እናም ለዚህ ትውልድ እንዲህ ይላል፥ እነሆ ጌታ ለጆሴፍ ስሚዝ፣ ዳግማዊ፣ ያሳ የውን ነገሮች አይቻለሁ እናም በእርግጥም እውነት እንደሆኑ ᵐአውቃለሁ፣ ምክንያ ቱም ተመልክቻቸዋለሁና፣ በሰው ሳይሆን በእግዚአብሔር ሀይል አይቻቸዋለሁና።

፳፮ እናም እኔ ጌታ አገልጋዬን ማርቲን ሀሪስን እነዚህን ነገሮች በተመለከተ ተመ ልክቻቸዋለሁ፣ በእግዚሐብሔር ሀይል አይቻቸዋለሁ ከማለት በስተቀር ምንም ተጨማሪ ነገር እንዳይነግራቸው አዝዘዋ ለሁ፤ እናም የሚናገራቸው ቃላት እነዚ ህን ናቸው።

፳፯ ነገር ግን ይህን ከካደ ቀደም ብሎ ከእኔ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን ያፈርሳል እናም እነሆ፣ ይኮነናል።

፳፰ እናም እራሱን ዝቅ አድርጎ እናም የሰ ራውን ስህተት ካልተቀበለ እና ትእዛዛቴን ለመጠበቅ ከእኔ ጋር ቃል ካልገባ፣ እና በእኔ ካላመነ በስተቀር፣ እነሆ፣ እንዲህ እለዋለሁ ምንም አይነት እይታ አይኖረውም፣ የተና ገርኳቸውን ነገሮች እይታ አልሰጠውምና።

፳፱ እናም ነገሩ ይህ ከሆነ፣ አገልጋዬ ጆሴፍ ካሁን በኋላ ምንም ነገር እንደማይ ሰራ እንዲሁም ስለዚህም ነገር ካሁን በኋላ እንዳያታክተኝ እንድትነግረው አዝሀለሁ።

፴ ነገሩ እንዲህ ከሆነ፣ እነሆ እንዲህ እል ሀለሁ ጆሴፍ፣ ጥቂት ገጾችን ከተረጎምህ በኋላ፣ ዳግም ትተረጉም ዘንድ ዳግመኛ እስከማዝህ ድረስ ለጥቂት ጊዜ ታቆማለህ።

፴፩ እናም ይህንን ካላደረግህ በስተቀር፣ ምንም ስጦታ አይኖርህም እናም የሰጠሁ ህን ነገሮች እወስዳቸዋለሁ።

፴፪ እናም፣ ምክንያቱም አንተን ለማጥ ፋት የታለመውን ዕቅድ አስቀድሜ ማየት ስለምችል፣ አዎን አገልጋዬ ማርቲን ሀሪስ ራሱን ዝቅ የማያደርግ ከሆነ እና ምስክር ነትን ከእጄ የማይቀበል ከሆነ ወደመተላ ለፍ እንደሚወድቅ አስቀድሜ አይቻለሁ፤

፴፫ እናም ሌሎች ብዙ አንተን ከምድር ላይ ᵐለማጥፋት የሚያቅዱ አሉ፤ እናም በዚህ ምክንያት ቀኖችህ ይራዘሙ ዘንድ ለአንተ እነዚህን ትእዛዛት ሰጥቻለሁ።

፴፬ አዎን፣ በዚህ ምክንያት እንዲህ ብያ ለሁ፣ እስከማዝህ ድረስ አቁም እናም ባለህ በት ሁን፣ እናም ያዘዝኩሁን ነገሮችን የም ታከናውንበትን ሁኔታዎች ᵐአዘጋጃለሁ።

፴፭ እናም ትእዛዛቴን በመጠበቅ ᵐታማኝ ከሆንህ፣ በመጨረሻው ቀን ᵃከፍ ትላለህ። አሜን።

፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. ታዛዥነት፣ ታዛዥ፣ መታዘዝ።
ለ አልማ ፳፡፲፫፣ ት. እና ቃ. ፮፡፴፣ ፻፴፭።
፳፫ ሀ ት. እና ቃ. ፭፡፩።
፳፬ ሀ "የሶስቱ ምስክሮች ምስክርነት"ን በመፅሐፈ ሞርሞን መጀመሪያ ገጾች ውስጥ ተመልከቱ።
፳፭ ሀ ኤተር ፭፡፫።
፴፫ ሀ ት. እና ቃ. ፲፡፮፣ ፴፡፴፣ ፴፰፡፴፰።
፴፬ ሀ ፩ ኔፊ ፫፡፯።
፴፭ ሀ ዘፀአ. ፲፭፡፳፮፣
ት. እና ቃ. ፲፩፡፳።
ለ ዮሐ. ፮፡፴፪–፴፣ ፩ ተሰ. ፬፡፣ ፲፯፣ ፫ ኔፊ ፲፭፡፩፣ ት. እና ቃ. ፱፡፲፬፣ ፲፯፡፳፣ ፳፭፡፲፮፣ ፳፪።

ክፍል ፤

ሚያዚያ ፲፯፲፯ (እ.አ.አ.) በሀርመኒ፣ ፔንስልቬንያ፣ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ እና ለኦሊቨር ካውድሪ የተሰጠ ራዕይ። በሚያዚያ ፤፣ ፲፯፲፯ (እ.አ.አ.) ኦሊቨር ካውድሪ የመፅሐፈ ሞርሞን ትርጉም ጸሐፊ በመሆን ማገልገል ጀመረ። የመፅሐፈ ሞርሞን መዛግብት የተቀረጹበትን ሰሌዳዎች በተመለከተ ስለነቢዩ ምስክርነት እውነትነት ቀደም ብሎ መለኮታዊ መገለጥን ተቀብሎ ነበር። ነቢዩ በኡሪ ምና ቱሚም ጌታን ጠየቀ እናም ይህን መልስ ተቀበለ።

፩–፤፣ በጌታ የእርሻ ስፍራ የሚያገለግሉ ሰራተኞች ደህንነትን ያገኛሉ፤ ፭–፲፫፣ ከደህንነት ስጦታ የበለጠ ስጦታ የለም፤ ፲፬–፳፤፣ የእውነት ምስክርነት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይመጣል፤ ፳፩–፳፯፣ ወደ ክርስቶስ ተመልከቱ እናም ሁልጊዜ መልካምን አድርጉ።

፩ ታላቅ እና ᵛድንቅ ስራ ወደ ሰዎች ልጆች ሊመጣ ነው።

፪ እነሆ፣ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ፈጣን እና ሀያል፣ ሁለት ስለት ካለው ሰይፍ ይልቅ ᵛየተሳለ፣ መገጣጠሚያን እና መቅኔን እስ ኪለይ ድረስ የሚሰራውን ᶮቃሌን አድምጡ፤ ስለዚህ ቃሎቼን አድምጡ።

፫ እነሆ፣ ᵛየእርሻው ስፍራ ነጭ ሆኖ አዝመራው ዝግጁ ነው፣ ስለዚህ፣ ለነ ፍሱም ዘለአለማዊ ደህንነት በእግዚአብ ሔር መንግስት ያከማች ዘንድ መሰብሰብ የሚሻ በኃይሉ ይጨድ እናም ቀኑም እየ መሸ ሳለም ይሰብስብ።

፬ አዎን፣ ማንኛውም ᵛየሚያጭድ እናም የሚሰበስብ፣ እንዲሁ በእግዚአብሔር የተ ጠራ ነው።

፭ ስለዚህ፣ እኔን ᵛብትጠይቁኝ ትቀበላላ ችሁ፣ ካንኳኳችሁ ይከፈትላችኋል።

፮ አሁን፣ እንደጠየቃችሁት፣ እነሆ፣ እን ዲህ እላችኋለሁ፣ ትእዛዛቴን ጠብቁ እናም ᵛየፅዮንን አስተሳሰብ ለማምጣት እና ለመ መስረት ᶮእሹ፤

፯ ᵛጥበብን እንጂ ᶮሀብትን ᶯአትሹ፣ እናም እነሆ፣ የእግዚአብሔር ᵐሚስጥራት ይገለጡላችኋል፣ እናም ባለጠጋም ትሆናላ ችሁ። እነሆ፣ ᵐዘለዓለማዊ ሕይወት ያለው እርሱም ባለጠጋ ነውና።

፰ እውነት፣ እውነት፣ እላችኋለሁ፣ ላደ ርግላችሁ እንደምትሹ እንዲሁ ይሆንላች ኋል፤ የምትሹ ከሆነም ካላችሁ፣ በዚህ ትውልድ ውስጥ ለብዙ መልካም ነገሮች መከናወን መሳሪያ ትሆናላችሁ።

፱ ለዚህ ትውልድ ᵛከንስሀ በቀር ሌላ ምንም አትናገሩ፤ ትእዛዛቴን ጠብቁ፣ እናም ስራዬን በትእዛዛቴ መሰረት ለማም ጣት እርዱ፣ እናም ትባረካላችሁ።

፲ እነሆ ስጦታ አላችሁ፣ እናም በስጦታ ችሁም የተነስ የተባረካችሁ ናችሁ። ᵛይህም የተቀደሰ እና ከላይ የመጣ መሆኑን አስታ ውሱ—

፤ ፩ ᵛ ኢሳ. ፳፱፡፲፰፤
ት. እና ቃ. ፬፣ ፲፰፡፳፬።
፪ ᵛ ሔሌ. ፮፡፳፱፤
ት. እና ቃ. ፴፮፡፩።
ᶮ ዕብ. ፭፡፲፪፤
ራዕ. ፩፡፲፤
ት. እና ቃ. ፳፤፡፩።
፫ ᵛ ዮሐ. ፬፡፴፭፤
ት. እና ቃ. ፴፩፡፬፣
፴፮፡፫፣ ፻፩፡፳፬።
፬ ᵛ ራዕ. ፲፡፲–፲፤
አልማ ፳፤፡፩፣
ት. እና ቃ. ፲፩፡፫–፬፣ ፳፤።
፭ ᵛ ማቴ. ፯፡፯–፳።
፮ ᵛ ᵐ.ᵐ. ፅዮን።
ᶮ ፩ ኔፊ ፲፫፡፴፤።
፯ ᵛ ᵐ.ᵐ. ጥበብ።
ᶮ ፩ ነገሥ. ፫፡፲–፲፫፣
ማቴ. ፲፤፡፳፣
ያዕቆ. ፪፡፲፳–፲፤።
ᵐ.ᵐ. ሀብቶች፣
አለማዊነት።
ᶯ አልማ ፴፤፡፲፬፣
ት. እና ቃ. ፳፳፡፴፩።
ᵐ ት. እና ቃ. ፵፪፡፳፩፣ ፳፭።
ᵐ.ᵐ. የእግዚአብሔር
ሚስጥሮች።
ᶰ ት. እና ቃ. ፲፬፡፯።
፱ ᵛ አልማ ፳፤፡፱፣
ት. እና ቃ. ፲፭፡፮፣ ፲፳፡፲፬–
፲፭፣ ፴፬፡፮።
ᵐ.ᵐ. መጸጸት፣ ንስሀ
መግባት፣
የሚስዮን ስራ።
፲ ᵛ ት. እና ቃ. ፳፫፡፳፩።

፲፩ እናም [ሀ]ከጠየቅህ፣ ታላቅ እና ድንቅ የሆኑ [ለ]ሚስጥራትን ታውቃለህ፤ ስለዚህም ሚስጥራትን ታውቅ ዘንድ፣ ብዙዎች ንም ወደ እውነት እውቀት ታመጣ ዘንድ፣ አዎን፣ የተሳሳተ መንገዳቸውን ሁሉ እን ዲተው [ሐ]ታሳምናቸውም ዘንድ [መ]ስጦታህን ትጠቀምበታለህ።

፲፪ በእንተ እምነት ውስጥ ካልሆኑ በስተ ቀር ስጦታህን ለማንም አታሳውቅ። [ሀ]በተ ቀደሱ ነገሮች አትቀልድ።

፲፫ መልካምን ካላደረግህ፣ እናም እስከ [ሀ]መጨረሻም [ለ]በእምነት [ሐ]ከጸናህ ከእግ ዚአብሔር የስጦታዎች ሁሉ የበላይ በሆ ነው በእግዚአብሔር መንግስት ትድናለህ፤ [መ]ከደህንነት በላይ የሆነ ምንም ስጦታ የለ ምና።

፲፬ እውነት፣ እውነት፣ እልሀለሁ፣ ባደ ረግኸው የተባረክህ ነህ፤ ምክንያቱም እኔን [ሀ]ጠይቀኃል እናም በጠየቅኸው መጠን የመ ንፈሴን መመሪያ ተቀብለኃል። ይህ ባይ ሆን ኖሮ አሁን ያለህበት ስፍራ ባልደረስህ ነበር።

፲፭ እነሆ፣ እንደጠየቅኸኝ ታውቃለህ እናም [ሀ]አዕምሮህን አብርቻለሁ፤ እናም አሁን በእውነት መንፈስ መረዳትን እንዳ ገኘህ ታውቅ ዘንድ እነዚህን ነገሮች እነግ ርሀለሁ፤

፲፮ አዎን፣ ከእግዚአብሔር በስተቀር ማንም ሀሳብህንና [ሀ]የልብህን ፈቃድ እንደ ማያውቅ [ለ]እንድታውቅ ዘንድ እነግርሀለሁ።

፲፯ እየጻፍህ ያለው ቃላት ወይም ስራ [ሀ]እውነት እንደሆነ—ለአንተ እንደምስክር ነት እነዚህን ነገሮች እነግርሀለሁ።

፲፰ ስለዚህ [ሀ]ትጉህ ሁን፤ በታማኝነት፣ ለቃሉ ሲል በሚገጥመው በማንኛውም አስቸጋሪ ሁኔታ ከአገልጋዬ ከጆሴፍ ጎን [ለ]ቁም።

፲፱ በስህተቱም ገስጸው፣ እናም ከእርሱም ተግሳጽን ተቀበል። ትዕግስተኛ ሁን፤ የተረ ጋጋህ ሁን፣ ራስህን ግዛ፣ ትዕግስት፣ እም ነት፣ ተስፋ እና ልግስና ይኑርህ።

፳ እነሆ፣ አንተ ኦሊቨር ነህ፣ እናም በፈ ቃድህ ምክንያት ተናግሬሀለሁ፤ ስለዚህ እነዚህን ቃላት በልብህ [ሀ]አከማች። የእግ ዚአብሔርን ትእዛዝ በመጠበቅታማኝ እና ትጉህ ሁን፣ እናም በፍቅሬ እቅፍ ውስጥም አደርግሀለሁ።

፳፩ እነሆ፣ እኔ [ሀ]የእግዚአብሔር ልጅ ኢየ ሱስ ክርስቶስ ነኝ። [ለ]የእኔው ወደሆኑት የመ ጣሁት እናም የራሴም ያልተቀበሉኝ እኔው ነኝ። እኔ በጭለማም የማበራ [ሐ]ብርሀን ነኝ፣ እናም [መ]ጭለማውም አይገነዘበውም።

፳፪ እውነት፣ እውነት፣ እልሀለሁ፣ ተጨ ማሪ ምስክርነትን ከፈለግህ፣ ስለ እነዚህ ነገ ሮች [ሀ]እውነትነት ታውቅ ዘንድ በልብህ ወደ እኔ የጮህክበትን ምሽት አስታውስ።

፳፫ ይህንን ነገር በተመለከተ ለአምሮህ [ሀ]ሰላምን አልተናገርኩምን? ከእግዚአብ ሔር ከመጣ ምስክርነት ይልቅ ምን አይ ነት [ለ]ምስክርነት ትፈልጋለህ?

፲፩ ሀ ት. እና ቃ. ፪፪፡፳፫፣
ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፲፰፣ ፳፯።
ለ ማቴ. ፲፩፡፳፭፣ ፲፫፡፲–፲፩፣
አልማ ፲፪፡፱።
ሐ ያዕ. ፭፡፳፣
አልማ ፳፪፡፣ ፴፭፣
ት. እና ቃ. ፲፳፡፴፱።
መ ቅ.መ.መ. ስጦታ፣
የመንፈስ ስጦታዎች።
፲፪ ሀ ማቴ. ፯፡፮።
፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. መፅናት።
ለ ሞዛያ ፪፡፴፭፣
ኤተር ፬፡፲፱፣
ት. እና ቃ. ፶፩፡፲፱፣
፳፫፡፴፯።
ሐ ፩ ኔፊ ፲፭፡፳፬።
መ ቅ.መ.መ. ደህንነት።
፲፬ ሀ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. አዕምሮ።
፲፮ ሀ ፩ ነገሥ. ፰፡፴፱።
ለ ፩ ዜና ፳፰፡፱፣
ማቴ. ፲፪፡፳፭፣
ዕብ. ፬፡፲፪፣
ሞዛያ ፳፬፡፲፪፣
፫ ኔፊ ፳፰፡፯።
ቅ.መ.መ. ሁሉን የሚያውቅ።
፲፯ ሀ ት. እና ቃ. ፲፡፱።
፲፰ ሀ ቅ.መ.መ. ትጋት።
ለ ት. እና ቃ. ፻፳፬፡፣ ፻፴–፻፴፯።
፳ ሀ ኤተር ፫፡፳፭፣
ት. እና ቃ. ፹፬፡፣ ፹፭።
፳፩ ሀ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ።
ለ ዮሐ. ፩፡፣ ፲–፲፪፣
የሐዋ. ፫፡፲፫–፲፯፣
፫ ኔፊ ፱፡፲፯፣
ት. እና ቃ. ፴፭፡፳።
ሐ ዮሐ. ፩፡፭፣
ት. እና ቃ. ፲፡፻፳።
ቅ.መ.መ. ብርሀን፣
የክርስቶስ ብርሀን።
መ ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ጭለማ።
፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. የመለየት ስጦታ።
፳፫ ሀ ቅ.መ.መ. ሰላም።
ለ ፩ ዮሐ. ፫፡፱፣
ት. እና ቃ. ፲፡፲፪።

፲፰ እናም አሁን፣ እነሆ፣ ምስክርነትን ተቀብለሀል፤ ሌላ ሰው የማያውቃቸውን ነገሮች ነግሬሀ ምስክርነትን አልተቀበልክምን?

፲፱ እናም፣ እነሆ፣ ከእኔም የምሻ ከሆነ ልክ እንደ አገልጋዬ ጆሴፍ ᵐትተረጉም ዘንድ ስጦታን እሰጥሀለሁ።

፳ እውነት፣ እውነት፣ እልሀለሁ፣ በሰዎች ᵐኃጢአት የተነሳ ያስቀረኋቸው አብዛኛውን ወንጌሌን የያዙ ᵃጽሁፎች አሉ።

፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. ማፅደቅ፣ ከበደል ነጻ መሆን።

፳ ይሁን እንጂ፣ በእምነት ሀየጸናው እና ፈቃዴንም የሚያደርገው፣ እርሱ ያሸንፋል፣ እናም በክብር የመለወጥ ቀን ሲመጣም ለውርሱን ይቀበላል

፳፩ እንዲሁም፣ ሙሉ ታሪኩን ገና ያልተቀበላችሁትን፣ ለሐዋሪያቴ ሀበተራራው ላይ ባሳየሁት ስርዓት ለምድር ሐበክብር ስትለወጥም፣ ውርሱን ይቀበላል።

፳፪ እናም አሁን፣ በእውነት እላችኋላሁ፣ እንደተናገርኳችሁ ፈቃዴን አሳውቃችኋለሁ፣ እነሆ እንድታውቁትም አደርጋለሁ፣ ይህም በትእዛዝ አይደለም ምክንያቱም ትእዛዛቴን የማያከብሩ ብዙዎች አሉና።

፳፫ ነገር ግን ትእዛዛቴን ለሚጠብቀው ለእርሱ የመንግስቴን ሀሚስጥራት እሰጠዋለሁ፣ እና በእርሱም ውስጥ ለዘለአለም ሕይወት ለየሚፈልቅ ሐየህያው ውኃ ምንጭ ይሆናል።

፳፬ እናም አሁን፣ እነሆ ይህም ጌታ አምላካችሁ ለቅዱሳኑ ያለው ፍላጎት ይህ ነው፣ ችኮላ የሚያመጣው ግራ መጋባት እንዳይኖር፣ በፍጥነት ሳይሆን፣ በፅዮን ምድር ራሳቸውን ይሰብስቡ።

፳፭ እነሆ፣ ሀየፅዮንን ምድር—እኔ ጌታ በእጆቼ ይዣታለሁ፤

፳፮ ይሁን እንጂ፣ እኔ ጌታም ሀየቄሣርን ለቄሣር አስረክቤአለሁ።

፳፯ ስለዚህ፣ እኔ ጌታ በአለም ትጠቀሙ ዘንድ፣ በአለምም የእኛ ነው የምትሉት እንዲኖራችሁ፣ እነርሱም በቁጣም እንዳይነሳሱባቸው፣ መሬቶች እንድትገዙ ፍቃዴ ነው።

፳፰ ሀሰይጣንም፣ ደምን እስከማፍሰስ ድረስም፣ እንዲያስቆጣቸው በልቦቻቸው ውስጥ ቁጣን ያነሳሳል።

፳፱ ስለዚህ፣ የፅዮን ምድርም በመግዛት ወይም በደም በስተቀር አይገኝም፣ አለበለዚያም ለእናንተ ምንም ውርስ የላችሁም።

፴ እና በመግዛትም ቢሆን፣ እነሆ የተባረካችሁ ናችሁ፤

፴፩ እናም በደምም ቢሆን፣ ደምን ለማፍሰስ ስለተከለከላችሁ፣ እነሆ፣ ጠላቶቻችሁ ያጠቋችኋል፣ እናም ከከተማ ወደ ከተማም፣ ከምኩራብ ወደ ምኩራብ ትቀጣላችሁ፣ እናም ውርስን ለመቀበል ጥቂቶች ብቻ ይቀራሉ።

፴፪ እኔ ጌታም በኃጢአተኞቹ ተቆጣሁ፤ መንፈሴንም ከምድር ኗሪዎች እከለክላለሁ።

፴፫ በቁጣዬም ማልሁ፣ እናም በምድርም ፊት ላይ ሀጦርነቶችን አወጅኩኝ፣ እናም ኃጢአተኛውም ኃጢአተኛውን ይገድላል፣ እናም ፍርሀትም በእያንዳንዱ ሰው ላይ ይመጣል፤

፴፬ እናም ሀቅዱሳንም ደግመው አያመልጡም፤ ይሁን እንጂ፣ እኔ ጌታ ከእነርሱ ጋር ነኝ፣ እና ከአባቴ ፊትም ከሰማይ ለእወርዳለሁ እናም ሐኃጢአተኞቹንም በማይጠፉ መእሳት አነዳቸዋለሁ።

፴፭ እናም እነሆ፣ ይህም ገና አይደለም፣ ነገር ግን በቅርቡ የሚሆን ነው።

፴፮ ስለዚህ፣ በምድር ላይ እነዚህን ነገሮች ሁሉ እኔ ጌታ በማወጄ ምክንያት፣ የእኔ ቅዱሳን ራሳቸውን በፅዮን ምድር መሰብሰባቸው ፍቃዴ ነው፤

፴፯ እናም እያንዳንዱ ሰው ሀፅድቅን በእ

፳ ሀ ት. እና ቃ. ፻፩፥፴፭።
ለ ማቴ. ፭፥፭፤
ት. እና ቃ. ፶፱፥፪፤
፹፰፥፳፭–፳፮።
፳፩ ሀ ማቴ. ፲፯፥፩–፫።
ለ ቅ.መ.መ. ምድር—የምድር የመጨረሻ ሁኔታ።
ሐ ቅ.መ.መ. አለም—የአለም መጨረሻ።
፳፫ ሀ አልማ ፲፪፥፱–፲፩፤
ት. እና ቃ. ፸፪፥፰፩፤
፹፬፥፲፱፤ ፻፯፥፲፰–፲፱።
ለ ዮሐ. ፬፥፲፬።
ሐ ቅ.መ.መ. ህያው ውሀ።
፳፭ ሀ ቅ.መ.መ. ፅዮን።
፳፮ ሀ ሉቃ. ፳፥፳፭፤
ት. እና ቃ. ፶፰፥፳፩–፳፫።
ቅ.መ.መ. መንግስት።
፳፰ ሀ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
፴፫ ሀ ቅ.መ.መ. ጦርነት።
፴፬ ሀ ቅ.መ.መ. ቅዱሳን።
ለ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
ሐ ማቴ. ፫፥፲፪፤
፪ ኔፊ ፳፮፥፮፤
ት. እና ቃ. ፵፭፥፶፯፤
፹፬፥፳፬፤ ፻፩፥፳፫–፳፭፤
፹፮።
ቅ.መ.መ. ክፉ፣ ክፋት።
መ ቅ.መ.መ. እሳት።
፴፯ ሀ ቅ.መ.መ. ጻድቅ፣ ጽድቅ።

ጆቹ እና ታማኝነትን በወገቡ ይውሰድ፣ እናም የማስጠንቀቂያ ^ድምፅም ወደ ምድር ኗሪዎች ይሰማ፤ እናም በቃል እና ፈጥኖ በመሄድ በስደት በኃጢአተኞች ላይ ሓክፉ ነገሮች እንደሚመጡ ይገለጹ።

፴፭ ስለዚህ፣ በከርትላንድ ውስጥ በዚህ እርሻ የሚኖሩት ደቀ መዛሙርቴ የስጋዊ ጉዳያቸውን ያዘጋጁ።

፴፮ አገልጋዬ ታይተስ ቢሊንግስ፣ በሚ መጣው ጸደይ፣ ትእዛዝ እስከምሰጣቸው ድረስ ከማይሄዱት ለራሴ ከምጠብቃቸው በስተቀር በዚህ ስፍራ ከሚኖሩት ጋር፣ ወደ ፅዮን ምድር ለመጓዝ መዘጋጀት እንዲችል፣ ሀላፊነት ያለበትን መሬትን ይሸጥ።

፴ እናም የሚቀረውም ገንዘብ ሁሉ፣ ብዙም ይሁን ጥቂት ግድ የለኝም፣ ወደ ፅዮን ምድር እንዲቀበሉ ለሾምኳቸው ይላክ።

፴፩ እነሆም እኔ ጌታ፣ ለአገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ ወደ ፅዮን ምድር የሚሄዱ ትን፣ እና በዚህም የሚቀሩትን ደቀ መዛ ሙርቴን ^ለመለየት የሚያስችለውን ሀይል እሰጠዋለሁ።

፴፪ እናም አገልጋዬ ኒውል ኬ ውትኒ የግ ምጃ ቤቱን፣ ወይም በሌላ ቃላት፣ የግምጃ ቤቱን በትንሽ ወቅት እንደያዘ ይቀጥል።

፴፫ ይሁን እንጂ፣ ለመስጠት የሚችለ ውን ገንዘብ ሁሉ ወደ ፅዮን ምድር እንዲ ላክ ይስጥ።

፴፬ እነሆ፣ እነዚህ ነገሮች በእጆቹ ውስጥ ናቸው፣ በጥበብም ያድርጋቸው።

፴፭ በእውነትም እላለሁ፣ ለሚቀሩ ትም ደቀ መዛሙርት ወኪል እንዲሆንም ይሾም፣ እናም ለዚህ ሀይልም ይሾም፤

፴፮ እናም አሁን፣ ከአገልጋዬ ኦሊቨር ካውድሪ ጋር፣ እነዚህን ነገሮች በማብራ ራት፣ ፈጥኖም ቤተክርስቲያኖችን ይጎ ብኝ። እነሆ፣ ገንዘብን እንደመራሁት ማግ ኘቱ ፍቃዴ ነው።

፴፯ ^ታማኝ የሆነው እና የሚጸናውም አለ ምን ያሸንፋል።

፴፰ ወደ ፅዮን ምድር ሀብትን የላከው በዚህ አለም ^ውርስን ይቀበላል፣ እናም ስራዎቹ ይከተሉታል፣ እናም በሚመጣው አለምም ዋጋው ይሰጠዋል።

፴፱ አዎን፣ እናም፣ ከእንግዲህ ወዲህ በጌታ ^የሚሞቱ ሙታን ብፁዓን ናቸው፣ ጌታ ሲመጣም፣ እና አሮጌው ነገሮች ^አል ፈው፣ እናም ሁሉም ነገሮች አዲስ ሲሆ ኑም፣ ከሞት ^ይነሳሉ እናም ከዚህም በኋላ ^አይሞቱምና፣ እናም በቅዱስ ከተማውም ከጌታም ውርስን ይቀበላሉ።

፴ እናም ጌታ ሲመጣ የሚኖረው፣ እና ሀይማኖትን የጠበቀውም፣ እርሱ ^የተባ ረከ ነው፤ ይሁን እንጂ በሰው እድሜ ^እን ዲሞትም ተወሰኖለታል።

፴፩ ስለዚህ፣ ልጆች እድሜአቸው እስ ኪገፋ ድረስም ^ያድጋሉ፤ ሽማግሌዎችም ይሞታሉ፤ ነገር ግን በምድርም ትቢያ ውስጥ አያንቀላፉም፣ ነገር ግን በቅጽበት ዓይንም ^ይለወጣሉ።

፴፪ ስለዚህ፣ ለዚህም ምክንያት ነው ሀዋ ሪያት ለአለም ስለሙታን ትንሳኤ የሰበ ኩት።

፴፫ እነዚህ ነገሮች ወደፊት መመልከት ያለባችሁ ነገሮች ናቸው፤ እናም፣ እንደ ጌታ አነጋገር፣ እናም በሚመጣው ጊዜም፣ እንዲሁም በሰው ልጅ ምፅዓት ቀን፣ አሁ ንም ^ቀርቧልና።

፴፬ እናም እስከዚያም ሰአት ድረስ በብልህ

፴፯ *ለ* ት. እና ቃ. ፭፡፱።
ሐ ኢሳ. ፴፯፡፲፩።
፴፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. የመለየት ስጦታ።
፴፯ *ሀ* ሞዛያ ፪፡፴፭፣
ት. እና ቃ. ፮፡፲፫።
፴፰ *ሀ* ት. እና ቃ. ፲፭፡፲፰።
፴፱ *ሀ* ራዕ. ፲፡፡፲፣
ት. እና ቃ. ፴፪፡፴፡–፴፯።
ለ ፪ ቆሮ. ፭፡፲፯።
ሐ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
መ ራዕ. ፳፭፡፱፣
አልማ ፲፭፡፴፭፣
ት. እና ቃ. ፹፰፡፲፲፯።
ቅ.መ.መ. የማይሞት፣
አለሟችነት።
፴ *ሀ* ቅ.መ.መ. መባረክ፣
የተባረከ፣ በረከት።
ለ ቅ.መ.መ. ስጋዊ ሞት።
፴፩ *ሀ* ኢሳ. ፳፭፡፰–፳፡፴፣
ት. እና ቃ. ፴፭፡፲፰፣
፲፩፡፳፡፴–፴፩።
ቅ.መ.መ. አንድ ሺህ አመት።
ለ ፩ ቆሮ. ፲፭፡፶–፶፪፣
ት. እና ቃ. ፴፫፡፴፪።
፴፫ *ሀ* ት. እና ቃ. ፴፭፡፲፭።

መካከል ሰነፎች ᵐደናግል ይኖራሉ፤ እናም በዚያም ሰዓት ጻድቃን ከኃጢአተኞቹ ሁሉ የሚለዩበት ይመጣል፤ እናም በዚያም ቀን ኃጢአተኞቹን ᵃነቅለው እንዲያወጡ እና በማይጠፋው እሳት ውስጥ እንዲወረውሯ ቸው መላእክቴን እልካለሁ።

፱ እናም አሁን እነሆ፣ እውነት እላች ኋለሁ፣ እኔ ጌታ በአገልጋዬ ᵐስድኒ ሪግ ደን አልተደሰትኩም፤ በልቡም ራሱን ᵃከፍ ከፍ ያደርጋል፣ እናም ምክርንም አልተቀ በለምና፣ ነገር ግን መንፈስንም አሳዝኗል፤

፲ ስለዚህ የእርሱ ᵐፅሑፍ በጌታ ዘንድ ተቀባይነት የለውም፣ እናም ሌላም ይጻፍ፤ እናም ጌታ ይህን ካልተቀበለውም፣ እነሆ በሾምኩበት ሹመትም አይቆምም።

፲፩ እና ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ በየዋህነት ኃጢአተኞችን ንስሀ እንዲገቡ ᵐለማስጠንቀቅ በልቦቻቸው ፍላጎት ᵃያላ ቸው፣ በዚህ ሀይልም ይሾሙ።

፲፪ ይህም፣ የብዙ ቃላት ቀን ሳይሆን፣ የማስጠንቀቂያ ቀን ነውና። እኔ ጌታም በመ ጨረሻዎቹ ቀናት ውስጥ አይዘበትብኝምና።

፲፫ እነሆ፣ እኔም ከበላይ ነኝ፣ እናም በበ ታችም ሀይሌ ይኖራል። ከሁሉም በላይ፣ እና በሁሉም የምሰራ፣ እናም በሁሉም የም ኖር ነኝ፣ እናም ሁሉንም ᵐእመረምራለሁ፣ እናም ሁሉም ነገሮች ለእኔ ተገዢ የሚሆኑ በትም ቀን ይመጣል።

፲፬ እነሆ፣ እኔ ᵐአልፋና ኦሜጋ፣ እንዲ ሁም ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ነኝ።

፲፭ ስለዚህ፣ ሁሉም ሰዎች እንዴት ᵐስሜን በከንፈሮቻቸው እንደሚይዙ ይጠ ንቀቁ—

፲፮ ምክንያቱም እነሆ፣ እውነት እላ ለሁ፣ የጌታን ስም በከንቱ የሚጠቀሙ፣ እናም ያለስልጣን የሚጠሩ፣ በዚህ እርግ ማን ውስጥ ያሉ ብዙዎች አሉ።

፲፯ ስለዚህ፣ ቤተክርስቲያን ለኃጢአ ታቸው ንስሀ ይግቡ፣ እናም እኔ ጌታ የእኔ አደርጋቸዋለሁ፤ አለበለዚያም ይቆረጣሉ።

፲፰ ከላይ የሚመጣውእርሱ ᵐቅዱስ እን ደሆነ፣ እናም በጥንቃቄ እና በመንፈስም ቁጥጥር ᵃመነገር እንዳለበትም አስታውሱ፤ እና በዚህም ውስጥ እርግማን የለም፣ እናም መንፈሱን የምትቀበሉት በጸሎት ᵃበኩል ነው፤ ስለዚህ፣ ይህ ባይሆን በእርግማን ይቀራሉ።

፲፱ ᵐበጸሎት በመንፈስ እንደተማሩት፣ አገልጋዮቼ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ እና ስድኒ ሪግደን ቤትን ይፈልጉባቸው።

፳ እነዚህ ᵐከሁሉም ይልቅ የዘለአለም ᵃክብርን፣ አለበለዚያም ታላቅን እርግ ማን፣ ይቀበሉ ዘንድ፣ እነዚህንም ነገሮች በትዕግስት ማሸነፍ ይቻል ዘንድ ነውና። አሜን።

ክፍል ፳፩

መስከረም ፲፭፣ ፲፰፻፴፭ (እ.አ.አ.)፣ በከርትላንድ ኦሀዮ ውስጥ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል ለቤተክርስቲያኗ ሽማግሌዎች የተሰጠ ራዕይ። በሚዙሪ ውስጥ እያለ ለሌላ ጊዜ ያስተላለፈውን የመፅሐፍ ቅዱስን ትርጉም ስራ ደግሞ ለመጀመር፣ ነቢዩ ወደ ሀይረም ኦሀዮ ለመሄድ እየተዘጋጀ ነበር። ወደ ፅዮን (ሚዙሪ) እንዲ

፩ ᵐ ማቴ. ፳፭፡፩–፲፫፤
ት. እና ቃ. ፵፭፡፹–፹፩።
ᵃ ሞዛያ ፲፮፡፪።
፪ ᵐ ቅ.መ.መ. ሪግደን፣ ስድኒ።
ᵃ ቅ.መ.መ. ኩራት።
፫ ᵐ ት. እና ቃ. ፹፡፣ ፹።
፬ ᵐ ት. እና ቃ. ፲፡፣ ፲፩–፲፭።
ቅ.መ.መ. ማስጠንቀቅ፣
ማስጠንቀቂያ፣
የሚስዮን ስራ።
ᵃ ት. እና ቃ. ፩፡፣ ፲–፲፭።
፭ ᵐ ᵃ ቆሮ. ፪፡፣ ፲።
ᵃ ᵐ ቅ.መ.መ. አልፋ እና ኦሜጋ።
፮ ᵐ ቅ.መ.መ. ማራከስ።
፯ ᵐ ቅ.መ.መ. ቅዱስ።
ᵃ ቅ.መ.መ. ማክበር።
ᵃ ት. እና ቃ. ፵፪፡፲፩።
፰ ᵐ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
፱ ᵐ ᵃ ቆሮ. ፩፡፲፯።
ᵃ ሮሜ ፰፡፲፣
ት. እና ቃ. ፶፣ ፩፣
፲፰፡፣ ፴፩።

ጓዙ የታዘዙት ወንድሞችም በጥቅምት ለመሄድ በቅንነት እየተዘጋጁ ነበር። በዚህ ስራ በበዛበት ጊዜ፣ ይህን ራዕይ ተቀብሎ ነበር።

፩–፲፩፣ በራሳቸው ታላቅ ኃጢአት እን ዳይቀር፣ ቅዱሳን እርስ በራሳቸውም ይቅር እንዲባባሉ ታዘዋል፤ ፲፪–፳፪፣ ንስሀ የማይገቡት በቤተክርስቲያና ለፍ ርድ ይቅረቡ፤ ፳፫–፳፭፣ አስራትን የሚ ከፍል በጌታ መምጫ ጊዜ አይቃጠልም፤ ፳፮–፴፪፣ ቅዱሳን እዳን እንዲያስወግዱ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል፤ ፴፫–፴፮፣ አመጸኞች ከፅዮን ውስጥ ይቆረጣሉ፤ ፴፯–፴፣ ቤተክርስቲያና አገሮችን ተፈርዳለች፤ ፴፩–፴፫፣ ፅዮን ታብባለች።

፩ እነሆ፣ ጌታ አምላካችሁ እንዲህ ይላች ኋል፣ አቤቱ እናንት የቤተክርስቲያኔ ሽማ ግሌዎች ሆይ፣ አድምጡ እናም ስሙ፣ እናም እኔ እናንተን በተመለከተ ያለኝን ፈቃድ ተቀበሉ።

፪ እውነት እላችኋለሁ፣ አለምን [1]እንድ ታሸንፉ እፈልጋለሁ፤ ስለዚህ፣ በእናንተ ላይ [2]ርህራሄ ይኖረኛል።

፫ በመካከላችሁ ኃጢአት የሰሩ አሉ፤ ነገር ግን በእውነት እላለሁ፣ አንድ ጊዜ፣ [3]ለክ ብሬ ስል፣ እናም ለነፍሳት ደህንነት ስል፣ ለኃጢአታችሁ [4]ይቅርታን አድርጌአለሁ።

፬ ለእናንተም መሀሪ እሆናለሁ፣ መንግስ ትንም ሰጥቻችኋለሁና።

፭ [5]ስርዓቶቼን እስካከበረ ድረስ፣ በህይ ወት እያለ፣ የመንግስቱ የሚስጥራት [6]ቁል ፎችም ከአገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ፣ በመሰረትኩበት መንገድ፣ አይወሰድበ ትም።

፮ በከንቱ በእርሱ ላይ ምክንያት የሚፈ ልጉበት አሉ፤

፯ ይሁን እንጂ፣ እርሱም ኃጢአትን ሰርቷል፤ ነገር ግን፣ እውነት እላችኋ ለሁ፣ ኃጢአታቸውን በፊቴ የሚናዘዙ፣ እና [7]ይቅርታን የሚጠይቁ፣ [8]ለሞት ኃጢ አትን ላልሰሩት፣ እኔ ጌታ [9]ይቅርታ አደ ርግላቸዋለሁ።

፰ ደቀ መዛሙርቶቼ፣ በቀደሙት ቀናት፣ እርስ በርሳቸው [10]ምክንያት ይፈልጉ ነበር እና በልቦቻቸውም ይቅርታን አያደርጉም ነበር፤ እናም በዚህ ክፉ ነገርም ተሰቃይተው እናም በምሬት [11]ተቀጥተው ነበር።

፱ ስለዚህ፣ እርስ በርሳችሁ [12]ይቅርታን መስጠት አለባችሁ እላችኋለሁ፤ ወንድሙ ለተላለፈው [13]ይቅርታን የማይሰጠው በጌታ ፊት ይኮነናል፤ ምክንያቱም በእርሱ ታላቁ ኃጢአት ይኖራልና።

፲ እኔ ጌታ [14]ይቅር የምለውን ይቅር እላ ለሁ፣ ነገር ግን እናንተ ለሁሉም ሰዎች [15]ይቅርታን ታደርጉ ዘንድ ይጠበቅባችኋል።

፲፩ እና በልባችሁም እንዲህ ማለት ይገባ ችኋል—በእኔ እና በአንተ መካከል እግዚ አብሔር [16]ይፍረድ፣ እናም [17]እንደስራህም ይከፍልህልና።

፲፪ እናም ለኃጢአቶቹ ንስሀ ያልገባ ውም፣ እና ያልተናዘዘውንም፣ [18]በቤተክ ርስቲያና ፊት አምጡት፣ እናም በቅዱሳን መጻህፍት ውስጥ በትእዛዝም ሆነ በራዕይ እንደሚላችሁም እንዲሁ አድርጉበት።

፲፫ እናም ይህንንም የምታደርጉት ለእግ

፰፬ ፪ *ሀ* ፩ ዮሐ. ፫፡፱።
ለ ቅ.መ.መ. ርህራሄ።
፫ *ሀ* ሙሴ ፩፡ ፴፱።
ለ ኢሳ. ፶፫፡ ፳፭።
፭ *ሀ* ቅ.መ.መ. ስነስርዓቶች።
ለ ት. እና ቃ. ፳፰፡ ፯፣
፹፬፡ ፲፱።
ቅ.መ.መ. የክህነት
ቁልፎች።
፯ *ሀ* ዘኁል. ፭፡ ፯–፲፣
ት. እና ቃ. ፲፱፡ ፳፣
፶፰፡ ፶፫።
ቅ.መ.መ. መገሰጽ።
ለ ት. እና ቃ. ፲፡ ፳፫–፳፮፣
ሐ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ስርየት፤
ይቅርታ ማድረግ።
፰ *ሀ* ቅ.መ.መ. ጸብ።
ለ ቅ.መ.መ. መገሰጽ፣ ተግሳጽ።
፱ *ሀ* ማር. ፲፩፡ ፳፭–፳፮፣
ት. እና ቃ. ፹፪፡ ፩።
ለ ማቴ. ፮፡ ፲፬–፲፭፣
ኤፌ. ፬፡ ፴፪።
፲ *ሀ* ዘፀአ. ፴፫፡ ፲፱፣
አልማ ፴፱፡ ፮፣
ት. እና ቃ. ፶፮፡ ፲፬።
ለ ሞዛያ ፳፮፡ ፳፱–፴፩።
፲፩ *ሀ* ፩ ሳሙ. ፳፬፡ ፲፪።
ለ ፪ ጢሞ. ፬፡ ፲፬።
፲፪ *ሀ* ት. እና ቃ. ፶፪፡ ፹–፹፫።

ዚአብሔር ክብር ነው፣ ይቅርታ ስላላደረጋ
ችሁ፣ ወይም ርህራሄ ስለሌላችሁ ሳይሆን፣
ነገር ግን በህግ ፊት ይህንኑ ለማረጋገጥ፣
ህግን የሰጣችሁን እንዳታስቀይሙ ነው—

፲፡ እውነት እላለሁ፣ በእነዚህ ምክንያቶች
እነዚህን ነገሮች አድርጉ።

፲፡፩ እነሆ፣ እኔ ጌታ አገልጋዬ በነበረው
ኤዝራ ቡዝ፣ እና ደግሞም በአገልጋዬ አይ
ዛክ ሞርሊ ተቆጥቻለሁ፣ ምክንያቱም ህግ
ንም ይሁን ትእዛዝን አላከበሩምና።

፲፡፪ በልቦቻቸው ክፋትን ፈልገዋል፣
እናም እኔ ጌታ መንፈሴን ከእነርሱ አርቄ
አለሁ። ክፉት የሌለባቸውን ነገሮች እንደ
ክፉ [a]ኮንነዋልና፤ ይሁን እንጂ፣ አገልጋዬን
አይዛክ ሞርሊን ይቅር ብዬዋለሁ።

፲፡፫ እና ደግሞም አገልጋዬ [b]ኤድዋርድ
ፓርትሪጅ፣ እነሆ፣ ኃጢአትን ሰርቷል፣
እናም [c]ሰይጣንም ነፍሱን ሊያጠፋ ይሻል
ነገር ግን፣ እነዚህን ነገሮች ሲያውቋቸው፣
እናም ለክፋታቸው ንስሀ ሲገቡ፣ ይቅርም
ይሰጣቸዋል።

፲፡፬ እናም አሁን፣ እውነትም እላለሁ፣
አገልጋዬ ስድኒ ጊልበርት፣ ከጥቂት ሳም
ንታት በኋላ ወደ ሀላፊነቱ፣ እና በፅዮን
ምድር ወዳለው ወኪሉ፣ ይመለስ ዘንድ
ፍቃዴ ነው፤

፲፡፭ እናም፣ እንዳይጠፉም፣ ያያቸውን
እና የሰማቸውን ነገሮች ደቀ መዛሙርቴ
እንዲያውቋቸው ያደርጋል። እናም በእዚ
ህም ምክንያት እነዚህን ነገሮች ተናግሬአ
ለሁና።

፲፡ እና እንዲህም እላችኋለሁ፣ አገልጋዬ
አይዛክ ሞርሊ ለመሸከም ከሚችለው በላይ
[d]እንዳይፈተን፣ እናም ሊጎዳችሁም የስህ
ተት ምክር እንዳይሰጥም፣ የእርሻ ቦታው
ይሸጥ ዘንድ አዘዝኩኝ።

፲፡፩ አገልጋዬ ፍሬድሪክ ጂ ዊልያምስ
የእርሻ ቦታውን መሸጡ የእኔ ፈቃድ አይ
ደለም፣ እኔ ጌታ፣ ኃጢአተኞችን በማ
ልጥልበት አምስት አመት ጊዜያት፣ በዚ
ህም የተወሰኑትን አድን ዘንድ፣ በከርት
ላንድ ምድር የምሽግ ስፍራን ለመጠበቅ
እፈልጋለሁና።

፲፡፪ እናም ከዚያ ቀን በኋላ፣ እኔ ጌታ ወደ
ፅዮን ምድር በተከፈተ ልብ የሚሄደውን
ማንንም እንደ [e]ጥፋተኛ አልቆጥርም፤ እኔ
ጌታ የሰው ልጆችን [f]ልብ እሻለሁና።

፲፡፫ እነሆ፣ አሁን እስከ ሰው ልጅ [g]ምፅ
ዓት ድረስ ቀኑም [h]ዛሬ ተብሎ ይጠራል፣
እናም እውነትም [i]የመስዋዕት ቀን ነው፣
እናም ህዝቤ አስራትን የሚከፍሉበትም ቀን
ነው፤ [j]አስራትን የሚከፍልም በእርሱ ምፅ
ዓት ጊዜ [k]አይቃጠልም።

፲፡፬ ከዛሬ በኋላ እንደ ምድጃ እሳት [l]የሚ
ነድ ቀን ይመጣልና—ይህም እንደ ጌታ አባ
ባል ነው—እውነትም እላለሁ፣ [m]ትዕቢተ
ኞችና ኃጢአትን የሚሠሩ ሁሉ ገለባ ይሆ
ናሉ፤ እናም አቃጥላቸዋለሁ፣ የሠራዊት
ጌታ እግዚአብሔር ነኝና፤ እናም [n]በባቢ
ሎን ውስጥ የሚቀሩትንም አላድንም።

፲፡፭ ስለዚህ፣ ካመናችሁኝ፣ ዛሬ ተብሎ
በሚጠራው ቀን ትሰራላችሁ።

፲፡፮ እናም አገልጋዬ [o]ኒወል ኬ ውትኒ እና
ስድኒ ጊልበርት በዚህ ያላቸውን ንብረት
እና [p]ግምጃዎቻቸውን መሸጣቸው አስፈ
ላጊ አይደለም፤ በዚህ ስፍራ ቤተክርስቲ

፲፡ [a] ፪ ኔፊ ፲፭፡ ፳፣
ት. እና ቃ. ፲፳፭፡ ፲፯።
፲፡ [b] ቅ.መ.መ. ፓርትሪጅ፣
ኤድዋርድ።
[c] ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
፲ [d] ቅ.መ.መ. መፈተን፣ ፈተና።
፲፡ [e] ቅ.መ.መ. በደል።
[f] ዘፀአ. ፴፭፡ ፭፣
ት. እና ቃ. ፶፱፡ ፲፭፣
፷፡ ፷፡።
፲ [g] ቅ.መ.መ. የኢየሱስ
ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
[h] ት. እና ቃ. ፵፭፡ ፮፣
፷፡ ፷፡–፷፭።
[i] ቅ.መ.መ. መስዋዕት።
[j] ሚል. ፫፡ ፲–፲፩።
ቅ.መ.መ. አስራት፣
አስራት መክፈል።
[k] ሚል. ፬፡ ፩፣
፫ ኔፊ ፳፭፡ ፩፣
ጆ.ስ.—ታ. ፩፡ ፴፯።
፲ [l] ኢሳ. ፴፮፡ ፲፭–፲፯።
ቅ.መ.መ. ምድር—ምድርን
ማፅዳት፣
አለም—የአለም መጨረሻ።
[m] ሚል. ፫፡ ፲፭፣
፪ ኔፊ ፲፪፡ ፲፪፣ ፳፫፡ ፲፩።
ቅ.መ.መ. ኩራት።
[n] ት. እና ቃ. ፩፡ ፲፮።
ቅ.መ.መ. ባቢሎን።
፲ [o] ቅ.መ.መ. ዊትኒ፣ ኒውል ኬ።
[p] ት. እና ቃ. ፶፮፡ ፳።

ያን የሚቀሩት ወደ ፅዮን ምድር ከመሄዳ ቸው በፊት ይህም ጥበብ አይደለምና።

፳፯ እነሆ፣ በህግጋቴ ውስጥ በጠላታችሁ ዘንድ ᐸእዳ አትግቡ ይላል፣ ወይም የተከ ለከለ ነው፤

፳፰ ነገር ግን እነሆ፣ በሚያስደስተው ጊዜ ጌታ አይወስድም፣ እናም መልካም በመሰ ለውም ይከፍላል አልተባለም።

፳፱ ስለዚህ፣ እናንት ወኪል ስለሆናችሁ፣ በጌታ መልእክት ትጓዛላችሁ፤ እናም እንደ ጌታ ፈቃድ በኩል የምታደርጉት ነገር ሁሉ የጌታ ስራ ነውና።

፴ እናም በእነዚህም የመጨረሻ ቀናት ለቅዱሳኑ፣ በፅዮን ምድር ᐸውርስን እንዲ ያገኙ ታደርጉ ዘንድ ተሹማችኋል።

፴፩ እናም እነሆ፣ ᐸቃላቴ እርግጥ በመ ሆናቸውና ^ስለማይወድቁ፣ እነርሱም እን ደሚያገኟቸው እኔ ጌታ እገልፅላችኋለሁ።

፴፪ ነገር ግን ሁሉም ነገሮች በጊዜአቸው ይከናወኑ ዘንድ ግድ ነው።

፴፫ ስለዚህ፣ መልካም ᐸራን ትሰሩ ዘንድ ᐸአትታክቱ፣ የታላቅ ስራን መሰረት እየገ ነባችሁ ነውና። እናም ^ከትትንሽ ነገሮች ታላቅ ነገሮች ይወጣሉና።

፴፬ እነሆ፣ ጌታ ᐸልብን እና መልካም ፈቃድ ያለውን አዕምሮ ^ይሻል፤ እናም ፈቃድ ያለው እና ᐸታዛዥ የሆነው እርሱ በእነዚህ በመጨረሻዎቹ ቀናት የፅዮንን ምድርን በረከት ይበላሉ።

፴፭ እናም ᐸአመጸኞችም ከፅዮን ምድር ^ይቆረጣሉ፣ እናም ተለይተው ይሄዳሉ፣ እናም ምድሩንም አይወርሱም።

፴፮ በእውነት እላለሁ፣ አመጸኞቹ ᐸከኤፍሬም ወገን አይደሉም፣ ስለዚህም ይነቀላሉ።

፴፯ እነሆ፣ እኔ ጌታ በእነዚህ በመጨረሻ ዎቹ ቀናት ቤተክርስቲያኔን በኮረብታ ላይ እንደተቀመጠ ዳኛ በአህዛብ ትፈርድ ዘንድ እንድትቀመጥ ሰርቻታለሁ።

፴፰ እንዲህም ይሆናል የፅዮን ኗሪዎች ፅዮንን በሚመለከቱ ነገሮችን ላይ ᐸበፍርድ ይቀመጣሉ።

፴፱ እናም ሐሰተኞች እና ግብዞች በእነርሱ ይፈተናሉ፣ እናም ᐸሐዋርያት እና ነቢያት ያልሆኑትም ይታወቃሉ።

፴ እናም ᐸዳኛ የሆነው ^ኤጲስ ቆጶስ እና አማካሪዎቹም፣ ^በሀላፊነታቸው ታማኝ ካልሆኑ፣ ይኮነናሉ፣ እናም ᐸሌሎችም በእነርሱ ስፍራ ይተከላሉ።

፴፩ እነሆ፣ እንዲህ እላችኋለሁ ᐸፅዮን ታብባለች፣ እናም የጌታም ^ክብር በእርሷ ላይ ያርፋል፤

፴፪ እናም እርሷም ለህዝብ ᐸምልክት ሆና ትቆማለች፣ እናም ከሰማይ በታች ካሉት ሀገሮች ውስጥም ወደ እርሷ ይመጣሉ።

፴፫ እናም በእርሷ ምክንያት የአለም ሀገ ሮች ሁሉ ᐸየሚንቀጠቀጡበት፣ እናም በአስፈሪዎቿም ምክንያት የሚደነግጡ በት ቀን ይመጣል። ጌታም ይህን ተናግ ሯል። አሜን።

፳፯ ᐸ ቅ.መ.መ. እዳ።
፴ ᐸ ት. እና ቃ. ፳፫፡፴፯።
፴፩ ᐸ ማር. ፲፫፡፴፩፣
፪ ኔፊ ፴፩፡፲፭፣
ት. እና ቃ. ፩፡፴፯–፴፰።
^ ት. እና ቃ. ፫፯፡፫።
፴፫ ᐸ ገላ. ፮፡፱።
^ ት. እና ቃ. የ፳፫፡፲፯።
፴፬ ᐸ ዘዳግ. ፴፪፡፴፮፣
ኢያ. ፳፪፡፭፣
ሞር. ፱፡፳፯።
ቅ.መ.መ. ልብ።
^ ሚክ. ፮፡፳።
ሐ ኢሳ. ፩፡፲፱።
ቅ.መ.መ. ታዛዥነት፣
ታዛዥ፣ መታዘዝ።
፴፭ ᐸ ቅ.መ.መ. አመጽ።
^ ት. እና ቃ. ፶፭፡፭፣
፶፡፳–፶፣ ፶፮፡፫።
ቅ.መ.መ. ውግዘት።
፴፮ ᐸ ዘዳግ. ፴፫፡፲፮–፲፯።
፴፯ ᐸ ኢሳ. ፪፡፫–፬፣
ት. እና ቃ. የ፴፫፡፳፭።
፴፱ ᐸ ራዕ. ፪፡፪።
ቅ.መ.መ. ሐዋሪያ።
፴ ᐸ ት. እና ቃ. ፶፳፡፲፯፣
የ፲፯፡፫–፫፬።
^ ቅ.መ.መ. ኤጲስ ቆጶስ።
ሐ ቅ.መ.መ. መጋቢ፣
መጋቢነት።
መ ት. እና ቃ. ፲፯፡፶፱–፷።
፴፩ ᐸ ቅ.መ.መ. ፅዮን።
^ ት. እና ቃ. ፴፭፡፳፯፣
፴፡፱–፲፣ ፶፯፡፲፭–፳።
ቅ.መ.መ. ክብር።
፴፪ ᐸ ቅ.መ.መ. ምልክት።
፴፫ ᐸ ኢሳ. ፳፡፲፣
ት. እና ቃ. ፶፯፡፲፱–፳።

ክፍል ፰፮

ጥቅምት ፴፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.)፣ በሀይረም ኦሀዮ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል ስለጻሎት የተሰጠ ራዕይ።

፩–፪፣ የእግዚአብሔር የመንግስቱ ቁልፎች በምድር ለሰው ተሰጥተዋል፣ እናም ወንጌሉም አሸናፊ ይሆናል፤ ፫–፮፣ የአንድ ሺህ ዘመን መንግስተ ሰማያት ይመጣል እናም በምድርም በእግዚአብሔር መንግስት ጋር ተዋሀዳለች።

፩ አድምጡ፣ እናም ሀያል እና ጠንካራ የሆነው፣ አካሄዱም እስከ ምድር ዳርቻ የሆነውን፣ አዎን ድምጹም ለሰዎች የሆነውን፣ ከላይም እንደተላከ ድምጽ የሆነውን፣ እነሆ—የጌታን መንገድ [a]አዘጋጁ፣ ጥርጊያውንም አቅኑ፤

፪ በምድርም ለሰው የእግዚአብሔር [b]መንግስት [c]ቁልፎችም ተሰጥተዋል፣ እናም ከዚህም ወንጌሉ፣ እጅም ሳይነካው ከተራራው ተፈንቅሎ ምድርን [d]እስከሚሞላ ድረስ እንደሚንከባለለውም [e]ድንጋይ፣ ወደ ምድር ዳርቻምይገፋል።

፫ አዎን፣ ድምፅም ይጮሀል—የጌታን መንገድ አዘጋጁ፣ የበጉን [f]እራት አዘጋጁ፣ [g]ለሙሽራውም ተዘጋጁ።

፬ ወደ ጌታም ጸልዩ፣ ቅዱስ ስሙንም ጥሩ፣ በአህዛብም መካከል ድንቅ ስራዎቹን እንዲታወቁ አድርጉ።

፭ የዚህች ኗሪዎችም እንዲቀበሉት፣ መንግስቱም በምድር ላይ እንዲሄድ፣ ጌታን ጥሩ፣ እናም የሰው ልጅ [h]የክብሩን ብርሀን [i]ለብሶ ከሰማይ በምድር ከተሰራችው የእግዚአብሔርን [j]መንግስት ጋር ለመገኛኘት [k]በሚገለጥበት ወደ ፊት ለሚመጡት ቀናትም ተዘጋጁ።

፮ ስለዚህ፣ [l]መንግስተ ሰማያት እንድት መጣ፣ የእግዚአብሔር [m]መንግስት ወደ ፊት ይሂድ፣ እንተም፣ እግዚአብሔር ሆይ፣ በሰማይም እንዳከበርህ እንዲሁ በምድርም ትከበር ዘንድ፣ ጠላቶችህም ይዋረዱ ዘንድ፤ ክብርም፣ ኃይልም፣ እና ግርማም [n]የአንተ ናትና፣ ከዘለአለም እስከዘለዓለም። አሜን።

ክፍል ፰፯

ጥቅምት ፳፱፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.)፣ በሂራም ኦሀዮ ውስጥ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ውልያም ኢ. መክለለን ለነቢሩት አምስት ጥያቄዎች መልስ በነቢዩ በኩል በሚስጥር እንዲመልስለት ጌታን ጠይቆ ነበር፣ እነዚህም ለጆሴፍ ስሚዝ የታወቁ አልነበሩም። በመክለለን ጥያቄ፣ ነቢዩ ጌታን ጠየቀ እና ይህን ራዕይ ተቀበለ።

፰፭ ፩ *ሀ* ኢሳ. ፶፡ ፫፡
ማቴ. ፫፡ ፫፡
ዮሐ. ፩፡ ፳፫።
፪ *ሀ* ት. እና ቃ. ፲፡ ፩–፭።
ለ ማቴ. ፲፮፡ ፲፱፡
ት. እና ቃ. ፵፪፡ ፰፱።
ቅ.መ.መ. የክህነት
ቁልፎች።
ሐ መዝ. ፸፪፡ ፲፱።
ቅ.መ.መ. የመጨረሻ ቀናት፣
የኋለኛው ቀናት፣
ዳንኤል—ትንቢተ ዳንኤል።
መ ዳን. ፪፡ ፴፬–፴፭።
፫ *ሀ* ማቴ. ፳፪፡ ፩–፲፡
ራዕ. ፲፱፡ ፱፡
ት. እና ቃ. ፶፰፡ ፲፩።
ለ ቅ.መ.መ. ሙሽራ።
፭ *ሀ* ቅ.መ.መ. ክብር።
ለ መዝ. ፺፣ ፡ ፩።
ሐ ዳን. ፪፡ ፴፱።
መ ማቴ. ፳፬፡ ፴።
፮ *ሀ* ራዕ. ፲፩፡ ፲፭።
ለ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር
መንግስት ወይም
መንግስተ ሰማያት።
ሐ ፩ ዜና ፳፱፡ ፲፩፡
ማቴ. ፮፡ ፲፣ ።

፩–፬፣ የወንጌሉ ሙሉነት ዘለአለማዊው ቃል ኪዳን ነው፤ ፭–፰፣ ሽማግሌዎች ይስበኩ፣ ይመስክሩ፣ እናም ከህዝብም ጋር ይወያዩ፤ ፱–፲፫፣ ታማኝ የወንጌል አገልግሎትም የዘለአለም ህይወትን ውርስ ያረጋግጣል።

፩ እነሆ፣ ጌታ ለአገልጋዬ ውልያም መክለለን እንዲህ ይላል—ከኃጢአቶችህ ዞር እስካልህ ድረስ፣ እና እውነቴን እስከተቀበልህ ድረስ የተባርክ ነህ፣ እንዲሁም በስሜ [ሀ]የሚያምኑት ሁሉ፣ ይላል ጌታ ቤዛህ፣ የአለም አዳኝ።

፪ እውነት እልሀለሁ፣ [ሀ]ዘለአለማዊ ቃል ኪዳኔን፣ እንዲሁም በነቢያት እና ሐዋርያት በቀደሙት ቀናት እንደተጻፈው፣ [ለ]ህይወት እንዲኖራቸው እና በመጨረሻዎቹም ቀናት የሚገለጡትን ክብሮች ተካፋይ ይሆኑ ዘንድ፣ ወደሰው ልጆች የተላከውን የወንጌሌን ሙሉነት በመቀበልህ የተባረክህ ነህ።

፫ በእውነትም እልሀለሁ፣ አገልጋዬ ውልያም ሆይ፣ አንተ፣ በሁሉም ባይሆን፣ ንጹህ ነህ፤ ስለዚህ በፊቴ ለማያስደስቱኝ ነገሮች ንስህ ግባ፣ ጌታ እነዚህን [ሀ]ያሳይሀልና።

፬ እናም አሁን፣ በእውነትም፣ እኔ ጌታ ስለአንተ በመመልከት ያለኝን ፈቃዴን፣ ወይም አንተን በተመለከተ ፈቃዴን አሳይህ ዘንድ እሻለሁ።

፭ እነሆ፣ በእውነትም እልሀለሁ፣ ከስፍራ ወደ ስፍራ፣ እና ከከተማ ወደ ከተማ፣ አዎን፣ ባልታወጁበት አካባቢዎች ውስጥ ሁሉ ወንጌሌን [ሀ]ታውጅ ዘንድ ፈቃዴ ነው።

፮ በዚህ ስፍራ ለብዙ ቀናት አትቆይ፤ ወደ ፅዮን አገርም ገና አትሂድ፣ ነገር ግን፣ ለመላክ የምትችለውን ላክ፤ አለበለዚያም፣ ስለ ንብረቶችህ አታስብ።

፯ ወደ ምስራቅ ባሉ ምድሮችም [ሀ]ተጓዝ፣ በእያንዳንዱም ስፍራዎች፣ ለእያንዳንዱም ሰው እናም በየምኩራቦቻቸው፣ ከህዝብ ጋር እየተወያየህ፣ [ለ]ምስክርነትህን ስጥ።

፰ አገልጋዬ ሳሙኤል ኤች ስሚዝም አብሮህ ይሂድ፣ እናም አትተወው፣ እናም አስተምረውም፤ እናም ታማኝ የሆነውም እርሱ በሁሉም ስፍራ [ሀ]ጠንካራ ይሆናል፤ እና እኔ ጌታም ከአንተ ጋር እሄዳለሁ።

፱ በታመሙትም ላይ [ሀ]እጆችህን ጫን፣ [ለ]ይድኑማል። እኔ ጌታ እስከምልክህ ድረስም አትመለስ። በስቃይህም ትእግስተኛ ሁን። [ሐ]ለምን፣ እናም ይሰጥሀል፤ አንኳኳ፣ ይከፈትልህማል።

፲ ብኩንነትን አትሻ። ከፅድቅ ያልሆኑውን ሁሉ ተው። የተፈተንህበትን [ሀ]አመንዝራትን አትፈጽም።

፲፩ እነዚህ ያዘዝኩህን [ሀ]ጠብቅ፣ እውነት እና ታማኝ ናቸውና፤ እናም ሀላፊነትህን ታጎላለህ፣ እናም የዘለአለም ደስታ [ለ]መዝሙሮች በራሳቸው ላይ ሆኖ ብዙ ህዝብን ወደ [ሐ]ፅዮን ትገፋለህ።

፲፪ እስከመጨረሻውም በእነዚህ ነገሮች [ሀ]ፅና፣ እናም በጸጋ እና በእውነት በተሞላው በአባቴም ቀኝ በኩልም የዘለአለም ህይወት [ለ]አክሊል ይኖርሀል።

፲፫ በእውነትም፣ እንዲህ ይላል ጌታ [ሀ]እግዚአብሔርህ፣ ቤዛህ፣ እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስ። አሜን።

፷፮ ፩ሀ ዮሐ. ፩፥፲፪።
ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
፪ሀ ቅ.መ.መ. አዲስ እና የዘለአለም ቃል ኪዳን።
ለ ዮሐ. ፲፥፲፤ ፫ ኔፊ ፭፥፲፫።
፫ሀ ያዕቆ. ፬፥፯፤ ኤተር ፲፪፥፳፯።
፭ሀ ማር. ፲፮፥፲፭።
፯ሀ ት. እና ቃ. ፸፭፥፮።
ለ ቅ.መ.መ. ምስክርነት።
፰ሀ ት. እና ቃ. ፶፪፥፲፯፤ ፻፴፫፥፶፰።
፱ሀ ቅ.መ.መ. ለታመሙት አገልግሎት መስጠት፤ እጅን መጫን።
ለ ማቴ. ፱፥፲፰።
ቅ.መ.መ. መፈወስ፣ ፈውሶች።
ሐ ያዕ. ፩፥፭።
፲ሀ ቅ.መ.መ. ማመንዘር።
፲፩ሀ ት. እና ቃ. ፻፭፥፳፬።
ለ ኢሳ. ፻፭፥፲፤ ት. እና ቃ. ፵፭፥፸፩።
ቅ.መ.መ. መዘመር።
ሐ ት. እና ቃ. ፲፩፥፮።
፲፪ሀ ፪ ጢሞ. ፫፥፲፬–፲፭፤ ፪ ኔፊ ፴፩፥፳።
ለ ኢሳ. ፳፪፥፫፤ ማቴ. ፳፭፥፳፩፤ ፩ ጴጥ. ፭፥፬።
፲፫ሀ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ—እግዚአብሔር ወልድ።

ክፍል ፰፤

ህዳር መጀመሪያ ፤፰፤፪፲፩ (እ.አ.አ.)፣ በሀይረም ኦሀዮ ውስጥ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። የልዩ ጉባኤ ጊዜ ነበር፣ እናም በነቢዩ በኩል ከጌታ የመጡት ራዕዮች መታተም ተወያይቶ ውሳኔም ተደርሶበት ነበር (የክፍል ፩ ርዕሰን ተመልከቱ)። ውልያም ደብሊው. ፌልፕስ የቤተክርስቲያኗን ማተሚያ በኢንድፔንደንስ፣ ምዙሪ መስርቶ ነበር። በጉባኤው ራዕዮችን በ Book of Commandments (መጽሐፈ ትእዛዛት) ለማተም እና ፤ ሺህ ቅጂዎች ለማተም ተወሰነ (ይህም ቀድሞ ባልታወቁ ችግሮች ምክንያት ወደ ፲ ሺህ ተቀንሶ ነበር)። ብዙ ወንድሞችም፣ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነትም እንደተገለጠላቸው፣ በዚያ ጊዜ ለመታተም የተሰበሰቡት ራዕዮች እውነት እንደሆኑ ምስክርነቶችን ሰጥተው ነበር። የጆሴፍ ስሚዝ ታሪክ እንደመዘገበው ክፍል ፩ ተብሎ የሚታወቀውን ራዕይ ከተቀበለ በኋላ፣ በራዕዮቹ ውስጥ የነበሩት ቃላት ጥቂት ንግግሮች ነበሩባቸው። ይህም ራዕይ ተከተለ።

፩–፲፣ ጌታ የሽማግሌዎችን ጸሎት ይሰማል እናም ይጠብቃቸዋል፤ ፲፩–፲፱፣ ከራዕዮቹ ጥቂቱን ክፍል እንዲያባዛለት ከጠቢባን አንዱን ጠየቀ፤ ፤–፤፲፣ ታማኝ ሽማግሌዎች በመንፈስ ህያው ይሆናሉ እናም የእግዚአብሔርንም ፊት ያያሉ።

፩ እናንት የቤተክርስቲያኔ ᵐሽማግሌዎች፣ በአንድነት የተሰበሰባችሁ፣ ጸሎቶቻችሁን የሰማሁ፣ ልባችሁንም የማውቅ፣ እና ልመናችሁም በፊቴ የሆነው፣ እነሆ እናም አድምጡ።

፪ እነሆ እናም አስተውሉ፣ ᵐአይኖቼ በእናንተ ላይ ናቸው፣ እናም ሰማያት እና ምድርም በእጆቼ ውስጥ ናቸው፣ እናም የዘለአለም ሀብትንም እሰጥ ዘንድ የእኔ ናቸው።

፫ ለእናንተ የቀረቡላችሁን በረከቶች ትቀበሉ ዘንድ እንደሚገባችሁ ለእምነታችሁ ተግታችኋል፤ ነገር ግን እነሆ፣ እውነት እላችኋለሁ በልባችሁ ᵐፍርሀት አለ፣ እናም በእውነት የማትቀበሉበት ምክንያቱ ይህ ነው።

፬ እናም አሁን እኔ ጌታ በፊት ለፊታችሁ የተቀመጡት ትእዛዛት እውነት እንደሆኑ ᵐምስክርነትን እሰጣችኋለሁ።

፭ አይኖቻችሁ በአገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ፣ ዳግማዊ ላይ ነበሩ፣ እናም ᵐቋንቋውን ታውቃላችሁ፣ እናም ፍጹም አለመሆኑን ታውቃላችሁ፣ እናም በልባችሁም ከቋንቋው በላይ ለመግለፅ እውቀት እንዲኖራችሁ ፈልጋችሁም ነበር፤ ይህንም ታውቃላችሁ።

፮ አሁን፣ በመፅሐፈ ትእዛዛት ውስጥ፣ እንዲሁም ከመካከሉ ታናሽ የሆነውንም ፈልጉ፣ እናም በመካከላችሁ ከሁሉም በላይ ᵐጠቢብ የሆነውንም ምረጡ፤

፯ ወይም፣ በመካከላችሁ እንደዚህ አንይነት ለመጻፍ የሚችል ማንም ቢኖር፣ ከዚያም እነዚህ እውነት እንደሆኑ አናውቅም በማለታችሁም መልካም አደረጋችሁ፤

፰ ነገር ግን፣ እንደዚህ አይነት አንድም መጻፍ ባትችሉ፣ እውነት እንደሆኑ ᵐባለ መመሰከራችሁም ትኮነናላችሁ።

፱ በውስጣቸው ᵐጽድቅ ያልሆነ እንደሌሉ ታውቃላችሁና፣ እናም ፅድቅ የሆነው ከላይ፣ ᶜከብርሀናት አባት ይመጣልና።

፲ እና ዳግም፣ እውነት እላችኋለሁ ይህ

፰ ᵃ፤ ᵇ፩ ᵃ ቅ.መ.መ. ᵐሽማግሌ።
ᵇ፩ᵃ መዝ. ፴፬፡፲፭።
ᶜ፩ᵃ ቅ.መ.መ. ፍርሀት።
ᵈ፩ᵃ ቅ.መ.መ. ምስክርነት፤ እውነት።
ᵉ፩ ᵃ ት.እና ቃ. ፩፡፳፬።
ᶠ፤ ᵃ ᵇ ኔፊ ፱፡፳፰–፳፱፣ ፴፪።
ᵍ፰ ᵃ ቅ.መ.መ. ምስክር።
ᵃ፱ ᵃ ሞሮኒ ፯፡፲፭–፲፰።
ᵃ ያዕ. ፩፡፲፤
ᵃ ት.እና ቃ. ፱፡፳፬፣ ᵇ፲፩፡ ᶜ፴፭፣ ᵈ፲፰፡ ᵉ፴፣ ᶠ፲፡ ᵍ፴፪።

እድላችሁ ነው፣ እናም ᵐከቅናት እና ᵃፍር ሀት ራሳችሁን ብታርቁ፣ እናም በፊቴም ᵃትሁት ብትሆኑ፣ ወደ አገልግሎቱ እን ደተሾማችሁ ቃል ኪዳንን እሰጣችኋለሁ፣ በብቃት ትሁት አይደላችሁምና፣ ᵐመጋረ ጃውም ይገፈፋል እናም ᵐአይታችሁኝም እኔ ማን እንደሆንኩም በሰውነት ወይም በስጋዊ አዕምሮ ሳይሆን፣ በመንፈስ ይህን ታውቃላችሁ።

፲፩ ማንም ᵐተፈጥሮአዊ ሰው በእግዚአ ብሔር ፊት፣ በስጋዊ አዕምሮም፣ ይቆም ዘንድ አይችልም።

፲፪ አሁንም በእግዚአብሔር ፊት፣ ወይም የመላእክትን አገልግሎት፣ ትመለከቱ ዘንድ አትችሉም፤ ስለዚህ፣ ᵐፍጹም እስክትሆ ኑም ድረስ ᵃበትዕግስት ፅኑ።

፲፫ አዕምሮዎቻችሁም ወደ ነበሩበት አይ መለሱ፤ እናም ᵐብቁ ስትሆኑም፣ በጊዜዬ፣ በአገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ እጆች በኩል የተሰጣችሁን ታያላችሁ እናም ታው ቃላችሁም። አሜን።

ክፍል ፰፰

ህዳር ፭፣ ፲፰፻፴፭ (እ.አ.አ.)፣ በሀይረም ኦሀዮ ውስጥ፣ ስለኦርሰን ሀይድ፣ ሉክ ኤስ ጆንሰን፣ ላይማን ኢ ጆንሰን፣ እና ውልያም ኢ መክለለን የጌታን ሀሳብ እን ዲታወቅ በቀረበው ልመና መልስ አማካይነት በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተ ሰጠ ራዕይ። ምንም እንኳን የዚህ ራዕይ ክፍል ለእነዚህ አራት ሽማግሌዎች የተ ሰጠ ቢሆንም፣ በውስጡ ያሉት አብዛኛዎቹ ለቤተክርስቲያኗ ሁሉ ተገቢ የሆኑ ናቸው። ይህ ራዕይ በ፲፰፻፴፭ (እ.አ.አ.) በትምህርት እና ቃል ኪዳን ቅጂ ውስጥ በታተመበት ጊዜ በጆሴፍ ስሚዝ አመራር ተስፋፍቶ ነበር።

፩–፭፣ ሽማግሌዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነ ሳስተው የተናገሩት ቅዱሳን መጻህፍት ናቸው፤ ፮–፲፪፣ ሽማግሌዎች ይስበኩ እናም ያጥምቁ፣ እናም በእውነት የሚ ያምኑትን ምልክቶች ይከተሏቸዋል፤ ፲፫–፳፩፣ ከአሮን ወንድ ልጆች መካከል በኩሩ በቀዳሚ አመራር ስር እንደ ኤጲስ ቆጶስ አመራር ያገለግላል (ይህም ማለት፣ እንደ ኤጲስ ቆጶስ የአመራር ቁልፎችን ይይዛል)፤ ፳፪–፳፰፣ ወላጆች ወንጌልን ለልጆቻቸው እንዲያስተምሩ ታዝዘዋል፤ ፳፱–፴፫፣ ቅዱሳን ሰንበትን ያክብሩ፣ በት ጋት ይስሩ፣ እናም ይጸልዩ።

፩ አገልጋዬ፣ ኦርሰን ሀይድ፣ በህያው እግዚአብሔር ᵐመንፈስ በኩል፣ ከህዝብ ወደ ህዝብ፣ ከምድር ወደ ምድር፣ በጎ ጢአተኞቹ ስብሰባዎች ውስጥ፣ በምኩራ ቦች ውስጥ፣ ምክንያቶችን በመስጠት እና ቅዱስ መጻህፍቶችን ሁሉ ለእነርሱ በማብ ራራት፣ ዘለአለማዊ ወንጌልን እንዲያውጅ በሹመት ተጠርቶ ነበር።

፲ ᵐ ቅ.መ.መ. ቅንዓት፣ መቅናት።
ᵃ ቅ.መ.መ. ፍርሀት።
ᵇ ቅ.መ.መ. ትሁት፣ ትሕትና።
ᶜ ቅ.መ.መ. ዐይነ-እርግብ።
ᵈ ት. እና ቃ. ፲፰፡ ፳፰፤ ፻፲፡ ፩፤ ፲፯፡ ፲፯።
፲፩ ᵐ ጆ.ስ.ት. ዘፀአ. ፴፲፡ ፳፣ ፳፲ (ተጨማሪ)፤ ዮሐ. ፩፡ ፲፰፣ ፲፯፡ ፲፯፤ ጆ.ስ.ት. ፩ ዮሐ. ፀ፡ ፲፪ (ተጨማሪ)፤ ት. እና ቃ. ፲፰፡ ፲ፀ–፲፱፣ ሙሴ ፩፡ ፲፩፣ ፲ፀ።
፲፪ ᵐ ሞዛያ ፫፡ ፲፱።
ᵃ ቅ.መ.መ. ፍጥረታዊ ሰው።
፲፫ ᵐ ማቴ. ፭፡ ፴፰፣ ፫ ኔፊ ፲፪፡ ፴፰።
ᵃ ሮሜ ፪፡ ፲።
ᵇ ቅ.መ.መ. ትዕግስት።
፲፬ ᵐ ቅ.መ.መ. ብቁ፣ ብቁነት።
፰፰ ፩ ᵐ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።

፪ እናም፣ እነሆ፣ እና ተልዕኮአቸው እንዲሄዱ ለተወሰነላቸው፣ በክህነት ለተሾሙት ሁሉ ይህም ምሳሌ ነው—

፫ እናም ይህም በመንፈስ ቅዱስ በመነሳሳት [ሀ]ለሚናገሩትም ምሳሌ ነው።

፬ እናም [ሀ]በመንፈስ ቅዱስ ሲነሳሱ የሚናገሩት ማንኛውም ነገር ቅዱሳን መጻህፍት ይሆናሉ፣ የጌታ ፈቃድም ይሆናል፣ የጌታ አዕምሮም ይሆናል፣ የጌታ ቃል ይሆናል፣ የጌታ ድምጽ፣ እናም ለደህንነት የእግዚአብሔር [ለ]ሀይልም ይሆናል።

፭ እነሆ፣ አገልጋዮቼ ሆይ፣ ይህም ለእናንተ የተሰጠ የጌታ ቃል ኪዳን ነው።

፮ ስለዚህ፣ ተደሰቱ፣ እናም [ሀ]አትፍሩ፣ እኔ ጌታ ከእናንተ ጋር ነኝና፣ እናም ከጎናችሁ እቆማለሁና፣ እና ስለ እኔም፣ እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስ፣ የህያው እግዚአብሔር ልጅ እንደሆንኩኝ፣ እስቀድሜም እንደነበርኩኝ፣ ህያውም እንደሆንኩኝ፣ እናም ዳግምም እንደምመጣ ትመሰክራላችሁ።

፯ ይህም ለአንተ አገልጋዬ [ሀ]ኦርሰን ሀይድ፣ እናም ለአገልጋዬ ሉክ ጆንሰንም፣ እናም ለአገልጋዬ ላይመን ጆንሰንም፣ እና ለአገልጋዬ ውልያም ኢ. መክለለንም፣ እናም ለቤተክርስቲያኔ ታማኝ ሽማግሌዎች ሁሉ የተሰጠ የጌታ ቃል ነው—

፰ ወደአለም ሁሉ [ሀ]ሂዱ፣ ለእያንዳንዱም [ለ]ፍጥረት፣ በሰጠኋችሁ [ሐ]ስልጣን እየሰራችሁ፣ በአብ፣ እና በወልድ፣ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም [መ]እያጠመቃችኋቸው ወንጌልን [ሠ]ስበኩ።

፱ እናም [ሀ]የሚያምን እና የተጠመቀ [ለ]ይድናል፣ እናም ያላመነ ግን [ሐ]ይፈረድበታል።

፲ እናም የሚያምነውም፣ እንደተጻፈው ይባረካል [ሀ]ምልክቶችም ይከተሉታል።

፲፩ እናም ለእናንተም የዘመኑን [ሀ]ምልክቶች፣ እናም የሰው ልጅ መምጫ ምልክቶች፣ ታውቁ ዘንድ ይሰጣችኋል፤

፲፪ እናም አብም የሚመሰክርላቸው ሁሉ፣ ለእናንተም እነርሱን ለዘለአለም [ሀ]የምታትሙባቸውን ሀይል ይሰጣችኋል። አሜን።

፲፫ እናም አሁን፣ ከቃል ኪዳኖች እና ከትእዛዛት በተጨማሪ ሌሎች ነገሮችን የሚመለከቱት፣ እነዚህ ናቸው—

፲፬ ጌታ በፈቀደ ጊዜ፣ እንደ መጀመሪያው ለማገልገል፣ ከዚህ በኋላ ለቤተክርስቲያኗ የሚሾሙ ሌሎች [ሀ]ኤጲስ ቆጶሳት አሉ፤

፲፭ ስለዚህ እነዚህም ብቁ የሆኑ [ሀ]ሊቀ ካህናት መሆን ይገባቸዋል፣ እናም፣ [ለ]የአሮን እውነተኛ ተወላጆች ካለሆኑ በስተቀር፣ በመልከ ጼዴቅ ክህነት [ሐ]ቀዳሚ አመራር በኩልም ይሾማሉ።

፲፮ እናም እነርሱም [ሀ]የአሮን እውነተኛ ተወላጆች ሊሆኑ፣ ከአሮን ወንድ ልጆች በኩር ከሆኑ፣ ለኤጲስ ቆጶስ አመራርነት ህጋዊ መብት አላቸው፤

፲፯ በኩሩም በዚህ ክህነት የአመራር መብትን፣ እናም የዚህንም [ሀ]ቁልፎች ወይም ስልጣናት ይይዛልና።

፲፰ የአሮን [ሀ]እውነተኛ ተወላጅ እና በኩር ካልሆነ በስተቀር፣ ማንም ሰው ለዚህ ሀላፊ

፫ ሀ ፪ ጴጥ. ፩፥፳፩፤
ት. እና ቃ. ፲፰፥፴፪፤
፹፪፥፲፮፤ ፪፥፭።
፬ ሀ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ፤
ራዕይ።
ለ ሮሜ ፩፥፲፮።
፮ ሀ ኢሳ. ፵፩፥፲።
፯ ሀ ቅ.መ.መ. ሀይድ፣ ኦርሰን።
፰ ሀ ት. እና ቃ. ፩፥፪፤ ፳፫፥፴፯።
ለ ማር. ፲፮፥፲፭።
ሐ ቅ.መ.መ. ስልጣን።
መ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣
መጥመቅ።
ሠ ቅ.መ.መ. መስበክ፤
የሚስዮን ስራ።
፱ ሀ ማር. ፲፮፥፲፮፤
ት. እና ቃ. ፳፥፳፭።
ለ ቅ.መ.መ. ደህንነት።
ሐ ቅ.መ.መ. ኩነኔ።
፲ ሀ ቅ.መ.መ. ምልክት።
፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. የጊዜዎች
ምልክቶች።
፲፪ ሀ ት. እና ቃ. ፩፥፰፤
፻፴፪፥፵፱።
ቅ.መ.መ. ማተም፣
ማስተሳሰር።
፲፬ ሀ ቅ.መ.መ. ኤጲስ ቆጶስ።
፲፭ ሀ ት. እና ቃ. ፸፪፥፩።
ለ ቅ.መ.መ. አሮን፣
የሙሴ ወንድም።
ሐ ቅ.መ.መ. ቀዳሚ አመራር።
፲፮ ሀ ት. እና ቃ. ፻፯፥፲፭–፲፯።
ቅ.መ.መ. አሮናዊ ክህነት።
፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
፲፰ ሀ ዘፀአ. ፴፥፲፪–፲፭፤
ት. እና ቃ. ፹፬፥፲፰፤
፻፯፥፲፫–፲፮፤ ፸–፸፮።

ነት፣ የዚህን ክህነት ቁልፎች ለመያዝ ህጋዊ መብት አይኖረውም።

፲፤ ነገር ግን፣ የመልከ ጼዴቅ ክህነት ᵇሊቀ ካህን በታናሾቹ ሀላፊነቶች ለማስተዳደር ስልጣን እንዳለው የአሮን እውነተኛ ተወ ላጅ እና በኩር በማይገኝበት ጊዜ፣ በመልከ ጼዴቅ ክህነት ቀዳሚ አመራር እጆች ስር ለዚህ ስልጣን ከተጠራ፣ እና ከተለየ እና ከተሾመ፣ ᵃበኤጲስ ቆጶስ ሀላፊነት ለማስ ተዳደር ይችላል።

፲፭ እና፣ ደግሞም፣ የአሮን እውነተኛ ተወ ላጅም በዚህ ቀዳሚ አመራር መመረጥ፣ እና በብቃት መገኘት፣ እናም ᵇመቀባት፣ እናም በአመራሩ እጆች ስር ᵃመሾም አለ ባቸው፣ አለበለዚያ በክህነት ስልጣናቸው ለማስተዳደር ህጋዊ ስልጣን አይኖራቸ ውም።

፲፮ ነገር ግን፣ ከአባት ወደ ልጅ በሚወረ ሰው ክህነት መብትን በሚመለከት በታ ወጀው መሰረትም፣ ተወላጅነታቸውን በሚ ያረጋግጡበት ጊዜ፣ ወይም ከላይ በተጠቀ ሱት አመራር እጆች ስር በጌታ ራዕይ ካገኙ፣ መቀባታቸውን ለማረጋገጥ ይችላሉ።

፲፯ እና ደግሞም፣ ለዚህ አገልግሎት የተለየ፣ ማንም ኤጲስ ቆጶስ ወይም ሊቀ ካህን፣ በቤተክርስቲያኗ ᵇቀዳሚ አመራር ፊት ካልሆነ በስተቀር፣ በወንጀል መኮነን ወይም ለፍርድ ሊቀርብ አይገባም፤

፲፰ እናም ጥርጣሬ በሌለው ምስክር በአ መራሩ ፊት ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝ፣ ይፈረ ድበታል፤

፲፱ እናም ንስሀ ቢገባ፣ በቤተክርስቲያኗ ቃል ኪዳኖች እና ትእዛዛት መሰረት ᵇይቅ ርታን ያገኛል።

፳ እና ደግሞም፣ ᵇወላጆች በፅዮን፣ ወይም በተደራጁት ᵃካስማዎቿ፣ ውስጥ ልጆች ኖሯቸው፣ ᶜስምንት አመት ሲሆ ናቸው፣ ስለ ንስሀ፣ በህያው እግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ እምነት፣ እናም ስለ ጥም ቀት እና እጆችን በመጫን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ስለመቀበል ትምህርትን ᵐባያስተ ማሯቸው፣ ᵐኃጢአቱ በወላጆች ራስ ላይ ይሆናል።

፳፩ ይህም ᵇለፅዮን፣ ወይም በማንኛውም በተደራጁት ካስማዎቿ፣ ኗሪዎች ህግም ነውና።

፳፪ እናም ልጆቻቸውም ለኃጢአቶ ቻቸው ᵇስርየት ᵃበስምንት አመታቸው ᶜይጠመቁ፣ እናም የእጆችንም መጫን ይቀበሉ።

፳፫ እናም ልጆቻቸውን ᵇእንዲጸልዩም፣ እናም በጌታ ፊት በቅንነት እንዲራመዱም ያስተምሩ።

፳፬ እናም የፅዮን ኗሪዎችም ᵇየሰንበትን ቀን ያክብሩ፣ ይቀድሱትም።

፳፭ እናም የፅዮን ኗሪዎችም፣ እንዲያገለ ግሉ እስከተጠሩ ድረስ፣ በሙሉ ታማኝነት አገልግሎታቸውንም ያስታውሱ፤ ስራ ፈት የሆነ እርሱ በጌታ ፊት ይታሰባልና።

፳፮ አሁን፣ እኔ ጌታ፣ በፅዮን ኗሪዎች አልተደሰትኩም፣ ᵇስራ ፈቶች በመካከ ላቸው አሉና፤ እናም ልጆቻቸውም ᵃበኃ ጢአት ውስጥ እያደጉ ናቸውና፤ ለዘለአ ለማዊ ሀብትም በቅንነት ᶜአይሹም፣ ነገር ግን አይኖቻቸው በስግብግብነት ተሞል ተዋል።

፳፯ እነዚህ ነገሮች መሆን አይገባቸውም፣ እናም ከመካከላቸው መወገድ አለባቸው፤

፲፤ ᵇ ቅ.መ.መ. ሊቀ ካህን።
ᵃ ቅ.መ.መ. ኤጲስ ቆጶስ።
፲፭ ᵇ ቅ.መ.መ. መቀባት።
ᵃ ቅ.መ.መ. መሾም፣ ሹመት።
፲፯ ᵇ ቅ.መ.መ. ቀዳሚ አመራር።
፲፰ ᵇ ቅ.መ.መ. ይቅርታ ማድረግ።
፲፱ ᵇ ቅ.መ.መ. ቤተሰብ—የወላጆች ሀላፊነቶች።
ᵃ ቅ.መ.መ. ካስማ።
ᶜ ት.እና ቃ. ፲፰፡ ፸፪፤ ፸፭፡ ፸፮።
ᵐ ቅ.መ.መ. ማስተማር፣ አስተማሪ።
ᵃ ያዕቆ. ፩፡ ፲፤፣ ት.እና ቃ. ፲፤፡ ፸፯–፸፰።
፳ ᵇ ቅ.መ.መ. ፅዮን።
ᵃ ቅ.መ.መ. መልስ መስጠት፣ ሂሳብ፣ ተጠያቂነት፣ ሀላፊነት።
ᶜ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣ መጥመቅ።
፳፪ ᵇ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
፳፫ ᵇ ት.እና ቃ. ፶፮፡ ፱–፲፫። ቅ.መ.መ. የሰንበት ቀን።
፳፭ ᵇ ቅ.መ.መ. ስራ ሰልቺ፣ ስራ ፈቺ።
ᵃ ቅ.መ.መ. ክፉ፣ ክፋት።
ᶜ ት.እና ቃ. ፮፡ ፲።

ስለዚህ፣ አገልጋዬ ኦሊቨር ካውድሪ እነዚ
ህን አባባሎች ወደ ፅዮን ምድር ይውሰድ።
፴፫ እናም ትእዛዝም እሰጣቸዋለሁ—በት
ክክለኛው ጊዜ በጌታ ፊት ᵐጸሎትን የማያ
ከናውነው እርሱ፣ በህዝቤ ዳኛ ፊት ᵃይታ
ሰብ።

፴፬ እነዚህ ᵐአባባሎች እውነተኛዎች እና
የታመኑ ናቸው፣ ስለዚህ አትተላለፏቸው፣
ወይም ᵃአታጉድሏቸውም።
፴፭ እነሆ፣ እኔ ᵐአልፋና ኦሜጋ ነኝ፣
እናም በቶሎ ᵃእመጣለሁ። አሜን።

ክፍል ፷፱

ህዳር ፲፩፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.)፣ በሀይረም ኦሀዮ ውስጥ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። በአጭር ጊዜ ለመታተም የታሰቡት የራዕይ ዝግጅቶች በህዳር ፩–፪ ልዩ ጉባኤ ላይ ጸድቀው ነበር። በህዳር ፫፣ በጓላም ተጨማሪ መግ ለጫ በመባል የታወቀው፣ በዚህ በክፍል ፲፰፣ ውስጥ ያለው ራዕይ ተጨምሮ ነበር። ኦሊቨር ካውድሪ የራዕዮች እና ትእዛዛት ዝግጅቶች ፅሁፎችን ወደ ኢንዲ ፔንደንስ ሚዙሪ ለመታተም እንዲወስድ ተመርጦ ነበር። የሚዙሪ ቤተክርስቲያ ንን ለመገንባት ተሰጥቶ የነበረውን ገንዘብም እንዲሁ መውሰድ ነበረበት። ይህም ራዕይ ጆን ዊትመር ከኦሊቨር ካውደሪ ጋር አብሮ እንዲሄድ መመሪያ ሰጥቷል እናም ዊትመር እንደ ቤተክርስቲያኗ የታሪክ ምሁር እና መዝጋቢ እንዲጓዝ እና ታሪካዊ ነገሮችን እንዲሰበስብ መመሪያ ሰጥቶ ነበር።

፩–፪፣ ጆን ዊትመር ኦሊቨር ካውድሪን ተከትሎ ወደ ሚዙሪ ይሂድ፣ ፫–፰፣ እር ሱም ይሰበክ፣ እና ታሪካዊ መረጃዎችን ይሰብስብ፣ እናም ይጻፍ።

፩ ለአገልጋዬ ᵐኦሊቨር ካውድሪ ጥቅ
ምም አድምጡኝ፣ ይላል ጌታ አምላካ
ችሁ። እውነተኛ እና ታማኝ የሆነ ከእርሱ
ጋር ካልሄደ በስተቀር፣ ወደ ፅዮን ምድር
ይዞ የሚሄዳቸውን ትእዛዛት እና ገንዘቦች
ለእርሱ በአደራ መስጠቱ በእኔ ዘንድ ጥበብ
አይደለም።
፪ ስለዚህ፣ እኔ ጌታ አገልጋዬ ᵐጆን ዊት
መር ከአገልጋዬ ኦሊቨር ካውድሪ ጋር
ይሄዱ ዘንድ ፍቃዴ ነው፤
፫ እና ደግሞም ስለቤተክርስቲያኔ የሚ
መለከታቸውን እና የሚያውቃቸውን አስ
ፈላጊ ነገሮች ሁሉ መጻፉን እና ᵐታሪክንም
መሰብሰቡን ይቀጥል፤
፬ እና ደግሞም ከኦሊቨር ካውድሪ እና
ከሌሎችም ᵐምክርን እና እርዳታን ይቀ
በል።
፭ እና ደግሞም፣ በአለም ያሉት አገል
ጋዮቼም ᵐየመጋቢነታቸውን መግለጫዎች
ወደ ምድረ ፅዮን ይላኩ፤
፮ ምድረ ፅዮንም የመቀበያ እና እነዚህ ነገ
ሮች ሁሉ የሚደረጉባት ዋና ስፍራ ናትና።
፯ ይሁን እንጂ፣ በቀላል እውቀትን እን
ዲያገኝ፣ አገልጋዬ ጆን ዊትመር፣ ከስፍራ
ወደ ስፍራ፣ እናም ከቤተክርስቲያኗ ወደ
ቤተክርስቲያኗ፣ ለብዙ ጊዜ ይጓዝ፣
፰ እየሰበከ እና እያብራራ፣ ለቤተክርስ

፴፫ ᵐ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
ᵃ ቅ.መ.መ. መገሰጽ፣ ተግሳጽ፤ ዳኛ፣ ፍርድ።
፴፬ ᵐ ራዕ. ፳፪፡፮፤ ፮።
ᵃ ት. እና ቃ. ፳፡ ፴፭፤ ፶፫፡ ፳፬–፳፭።
፴፭ ᵐ ቅ.መ.መ. አልፋ እና ኦሜጋ።
ᵃ ት. እና ቃ. ፩፡ ፲፪።
፷፱ ፩ ᵐ ቅ.መ.መ. ካውደሪ፣ ኦልቨር።
፪ ᵐ ቅ.መ.መ. ዊትመር፣ ጆን።
፫ ᵐ ት. እና ቃ. ፴፯፡ ፩–፫፤ ፹፭፡ ፩።
፬ ᵐ ቅ.መ.መ. ምክር (ስም)።
፭ ᵐ ቅ.መ.መ. መጋቢ፣ መጋቢነት።

ቲያኗ ጥቅም እና ᐟᐟበፅዮን ምድር ለሚያድጉት የሚቀጥሉት ትውልዶች እስከዘለአለም ይይዟቸው ዘንድ ከትውልድ ወደ ትውልድም ጥቅም እንዲሆንላቸው፣ ሁሉንም ነገሮች እያባዛ፣ እየመረጠ፣ እና እያገኘ ለብዙ ጊዜ ይጓዝ። አሜን።

ክፍል ፸

ህዳር ፲፪፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.)፣ በሀይረም ኦሀዮ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። የነቢዩ ታሪክ እንደሚገልጸው ከህዳር ፩ እስከ ፲፪ አራት ልዩ ጉባኤዎች ተካሂደዋል። በእነዚህም ስብሰባዎች ማብቂያ ላይ፣ በኋላም እንደ የ Book of Commandments (መፅሐፈ ትእዛዛት) እና ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች የታተሙት ራዕዮች ታላቅ አስፈላጊነት ታሰበበት። ይህም ራዕይ የተሰጠው ጉባኤው እነዚህን ራዕዮች "ለቤተክርስቲያኗ ከአለም ሁሉ ሀብቶች በላይ ታላቅ ዋጋ እንዳላቸው" በድምጽ ምርጫ ከተሰጠ በኋላ ነበር። የጆሴፍ ስሚዝ ታሪክ ስለዚህ ራዕይ "የአዳኛችን መንግስት ሚስጥር ቁልፎች ለሰው በአደራ እንደተሰጡ በማሳየት፣ በእነዚህ የመጨረሻዎቹ ቀናት የቤተክርስቲያኗ መሰረት፣ እና ለአለምም ጥቅም" የሚሆን ነው ብሎታል።

፩–፭፣ ራዕዮችን እንዲያትሙ መጋቢዎች ተመርጠዋል፤ ፮–፲፫፣ በመንፈሳዊ ነገሮች የሚያገለግሉ ደሞዛቸው ይገባቸዋል፤ ፲፬–፲፰፣ ቅዱሳን በስጋዊ ነገሮች እኩል መሆን አለባቸው።

፩ እነሆ፣ እና አድምጡ፣ እናንት የፅዮን ኗሪዎች፣ እናም በሩቅ ያላችሁ የቤተክርስቲያኔ ህዝብ፣ እናም ለአገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ፣ ለአገልጋዬ ማርቲን ሀሪስ፣ እና ደግሞም ለአገልጋዬ ኦሊቨር ካውድሪ፣ እና ደግሞም ለአገልጋዬ ጆን ዊትመር፣ ለአገልጋዬ ስድኒ ሪግደን፣ እና ደግሞም ለአገልጋዬ ውልያም ደብሊው ፌልፕስ በትእዛዝ መንገድ የምሰጣቸውን የጌታን ቃል ስሙ።

፪ ትእዛዝ እሰጣቸዋለሁና፤ ስለዚህ፣ አድምጡ እናም ስሙ፣ ጌታ እንዲህ ይላቸዋልና—

፫ እኔ ጌታ መርጫቸዋለሁ፣ እናም በሰጠኋቸው፣ እና ከዚህም በኋላ ለምሰጣቸው ራዕዮች እና ትእዛዛት ᐟᐟመጋቢዎች እንዲሆኑ ሾሜአቸዋለሁ፤

፬ እናም የዚህን የመጋቢነትን ዘገባ በፍርድ ቀን እፈልግባቸዋለሁ።

፭ ስለዚህ፣ እኔም መርጫቸዋለሁ፣ እናም እነዚህን የሚመለከቱትን ጥቅሞቻቸውን፣ አዎን ቅሬታዎችን ማስተዳደር፣ በእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ውስጥ ይህም ሀላፊነታቸው ነው።

፮ ስለዚህ፣ እነዚህን ነገሮች ለቤተክርስቲያኗም ሆነ ለአለም እንዳይሰጡ ትእዛዝ እሰጣቸዋለሁ፤

፯ ይሁን እንጂ፣ ከመሰረታዊ ፍላጎቶቻቸው እና መሻታቸው በላይ እስከተቀበሉ ድረስ፣ ወደ ᐟᐟጎተራዬ ያግቡ፤

፰ እናም፣ እንደ መንግስት ህግጋት ᐟᐟወራሾች እስከ ሆኑ ድረስ፣ ጥቅሙም ለፅዮን ኗሪዎች፣ እናም ለትውልዶቻቸው፣ የተቀደሰ ይሆናል።

፱ እነሆ፣ ጌታ ከእያንዳንዱ ሰው፣ እንዲሁም እኔ ጌታ እንደመደብኩት ወይም

ከዚህ በኋላ ለእያንዳንዱ ሰው እንደ ምመድበው፣ ᵐበመጋቢነቱ የምጠብቅበት ይህ ነው።

፲ እናም እነሆ፣ በህያው እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን አባል የሆነ ከእነዚህ የህግ ግዴታዎች ነጻ የሆነ ማንም የለም፤

፲፩ አዎን፣ ኤጲስ ቆጶስ ወይም የጌታን ጎተራን የሚጠብቀው ᵐወኪል፣ ወይም በስጋዊ ነገሮች ላይ መጋቢነት የተሰጠውም ቢሆን ከእነዚህ የህግ ግዴታዎች ነጻ አይደሉም።

፲፪ ለመንፈሳዊ ጉዳዮችንም ሊያስተዳድር የተመረጠውም፣ ለስጋዊ ጉዳዮች አስተዳደር መጋቢነት እንደተሰጣቸው ሁሉ፣ እርሱም ᵐደሞዙ ይገባዋል፤

፲፫ አዎን፣ እንዲሁም በብዛትም፣ ይህ ብዛትም ለእነርሱ በመንፈስ መግለጥ በኩል ይጨመርላቸዋል።

፲፬ ይሁን እንጂ፣ በስጋዊ ነገሮች ᵐእኩል ሁኑ፣ እናም ይህንንም በመሰሰት አይደለም፣ አለበለዚያም፣ የመንፈስ መገለጥ ብዛቱ ይከለከላልና።

፲፭ በእዚህ እያሉ አገልጋዮቼ በረከቴ በላያቸው እንዲገለጥ እና ᵐበትጋታቸው ምላሽ እና ለደህንነታቸው እንዲሁም ለጥቅማቸው ይህን ᶜትእዛዝም እሰጣቸዋለሁ፤

፲፮ ለምግብ እና ᵐለልብስ፣ ለውርስ፣ ለቤቶች እና መሬትም እኔ ጌታ ባስቀመጥኳቸው ስፍራ ሁሉ እና በምልካቸው በማንኛቸውም ስፍራ ይሆኑ ዘንድ ይህን ትእዛዝም እሰጣቸዋለሁ።

፲፯ ᵐበብዙ ነገሮች ታማኝ ነበሩና፣ እናም ኃጢአትንም ባለመስራት ድረስ በጎን ነገር አድርገዋልና።

፲፰ እነሆ፣ እኔ ጌታ ᵐመሐሪ ነኝ እናም እባርካቸዋለሁ፣ እናም ወደ እነዚህ ነገሮች ደስታም ይገባሉ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፳፭

ታህሳስ ፭፣ ፲፰፻፴፭ (እ.አ.አ.)፣ በሀይረም ኦሀዮ ውስጥ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ይህን ራዕይ እስከሚቀበል ድረስ ነቢዩ ከጸሀፊው ከሰ ድኒ ሪግደን ጋር መፅሐፍ ቅዱስን መተርጎም ቀጥሎ ነበር፣ በጊዜውም ይህም በዚህ የተሰጣቸውን መመሪያዎች ያሟሉ ዘንድ ትርጉምን ለጥቂት ጊዜ አቁመው ነበር። ቤተክርስቲያኗን የካደው እዝራ ቡዝ በጻፋቸው ደብዳቤዎች ምክን ያት በቤተክርስቲያኗ ላይ የነበረውን የጥላቻ ስሜት ለማቃለል ወንድሞች ለመ ስበክ ሊሄዱ ይገባል።

፭–፱፣ ጆሴፍ ስሚዝ እና ሰድኒ ሪግደን ወን ጌሉን እንዲያውጁ ተልከዋል፤ ፮–፲፭፣ የቅዱሳኑ ጠላቶችም ያፍራሉ።

፭ እነሆ፣ ለእናንተ አገልጋዮቼ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ እና ᵐስድኒ ሪግደን ጌታ እንዲህ ይላል፣ በእውነትም አንደበታችሁን ከፍታችሁ፣ እንደተሰጣችሁ መንፈስ እና ሀይል፣ እንዲሁም በፈቃዴ ወን ጌሌን ᶜየምትሰብኩበት፣ የመንግስቱንም ነገሮች፣ ᵈሚስጥራት ከቅዱስ መጻህፍቶች ውስጥ የምታብራሩበት አስፈላጊ እና

ᵐ ሀ ቅ.መ.መ. መጋቢ፣ መጋቢነት።
፲፩ ሀ ት.እና ቃ. ፶፯፡ ፮።
፲፪ ሀ ሉቃ. ፲፡ ፮።
፲፫ ሀ ት.እና ቃ. ፵፱፡ ፳።
ᶜ ቅ.መ.መ. መቀደስ፣ የቅድስና ህግ።
፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. ትጋት።
ᵈ ዘዳግ. ፲፡ ፲፪–፲፫።
፲፮ ሀ ት.እና ቃ. ፶፱፡ ፲፯–፳።
፲፯ ሀ ማቴ. ፳፭፡ ፳፭–፳፫።
፲፰ ሀ ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።
፳፭ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. ሪግደን፣ ስድኒ።
ᵉ ቅ.መ.መ. የሚስዮን ስራ።
ᶠ ት.እና ቃ. ፵፪፡ ፳፭፣ ፳፭።

በእኔም ጠቃሚ መስሎ የሚታይበት ጊዜ መጥቷል።

፪ እውነት እላችኋለሁ፣ በየአካባቢው ላሉት ለአለም እና ለቤተክርስቲያኗም፣ ለአንድ ወቅት፣ እንዲሁም እንድታውቁት እስከሚደረግ ድረስ አውጁ።

፫ በእውነት፣ ይህም የሰጠኋችሁ የወቅቱ ተልዕኮ ነው።

፬ ስለዚህ፣ በወይን ስፍራዬ አገልግሉ። የምድር ኗሪዎችንም ጥሯቸው፣ እናም መስክሩ፣ እናም ለሚመጡት ትእዛዛት እና ራዕዮችም መንገድን አዘጋጁ።

፭ አሁን፣ እነሆ ይህም ጥበብ ነው፤ የሚያነበውም [a]ይረዳው እና ደግሞም [b]ይቀበለውም፤

፮ ለሚቀበለውም ለእርሱ [c]በብዛት፣ እንዲሁም ሀይል ይሰጠዋልም።

፯ ስለዚህ፣ ጠላታችሁን [d]አሳፍሩ፤ በግልጽ እናም በግል [e]እንዲያገኟችሁ ጥሯቸው፤ እናም ታማኝ ብትሆኑ እፍረታቸው ይገለጣል።

፰ ስለዚህ፣ ብርቱ ማስረጃቸውን በጌታ ላይ ያምጡ።

፱ በእውነትም፣ ጌታ እንዲህ ይላችኋል—በእናንተ ላይ እንዳትበለጽጉ የሚከላከል [f]መሳሪያ አይከናወንም፤

፲ እናም ማንም ሰው በእናንተ ላይ ድምጹን ቢያነሳ እኔ በወሰንኩት ጊዜ ያፍራል።

፲፩ ስለዚህ፣ ትእዛዛቴን ጠብቁ፤ እውነተኛ እና ታማኝ ናቸውና። እንዲሁም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፷፪

በታህሳስ ፬፣ ፲፰፻፳፭ (እ.አ.አ.)፣ በከርትላንድ ኦሀዮ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ብዙ ሽማግሌዎች እና አባላት ሀላፊነታቸውን ለመማር እና በቤተክርስቲያኗ ትምህርቶች ለመታነፅ ተሰብስበው ነበር። ይህ ክፍል በአንድ ቀን የተሰጡ ሶስት ራዕዮች የተቀናጁበት ነው። ከ፩ እስከ ፰ ያሉት ቁጥሮች ኒዌል ኬ ውትኒ እንደ ኤጲስ ቆጶስ የተጠራበትን ያሳውቃሉ። ከዚያም ተጠራ እና ተሾመ፣ ከዚያም፣ ስለ ኤጲስ ቆጶሱ ሀላፊነቶች ተጨማሪ ማስረጃዎች የሚሰጡበትን ከቁጥር ፱ እስከ ፳፫ ያለውንም ተቀብሎ ነበር። ከዚህም በኋላ፣ ከቁጥር ፳፬ እስከ ፳፮ ስለፅዮን መሰብሰብ መመሪያ ሰጥተው ነበር

፩–፳፡ ሽማግሌዎች የመጋቢነታቸውን መግለጫ ለኤጲስ ቆጶሱ ይስጡ፤ ፱–፲፭፣ ኤጲስ ቆጶሱ ግምጃ ቤትን ይጠብቃል፣ እናም ድሆችን እና ችግረኞችን የሚሹት ይንከባከባል፤ ፲፮–፳፮፣ ኤጲስ ቆጶሳት የሽማግሌዎችን ብቃነት ያረጋግጡ።

፩ አድምጡ፣ እናም [g]መንግስት እና ሀይል የተሰጣችሁ አቤቱ እናንት የተሰባሰባችሁት የቤተክርስቲያኔ [h]ሊቀ ካህና ትየጌታን ድምፅ ስሙ።

፪ በእውነትም ጌታ እንዲህ ይላል፣ ለእናንተ፣ ወይም ከእናንት በዚህ የጌታ የወይን ስፍራ በሆነች ቤተክርስቲያን፣ [i]ኤጲስ ቆጶስ ይመረጥ ፍቃዴ ነው።

፫ እናም በእውነት በዚህም ነገር ያደረጋችሁት ጥበብ ነው፣ ከእያንዳንዱ [j]መጋቢ እጅ፣ በጊዜም ይሁን በዘለአለም፣ [k]የመ

፩ [a] ሀ ቅ.መ.መ. ማስተዋል።
[b] ለ አልማ ፲፪፡፱–፲፩።
[c] ሀ ማቴ. ፲፫፡፲፪።
[d] ሀ ሙሴ ፯፡፲፫–፲፯።
[e] ለ ት. እና ቃ. ፳፫፡፴፯፣ ፴፯፣ ፴፰–፴፱፣ ፴፱–፵፡ ሀ ቅ.መ.መ. ማስተዋል።
[f] ሀ ኢሳ. ፶፬፡፲፯።
[g] ሀ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር መንግስት ወይም መንግስተ ሰማያት።
[h] ለ ት. እና ቃ. ፳፫፡፲፬–፲፱።
[i] ሀ ቅ.መ.መ. ኤጲስ ቆጶስ።
[j] ሀ ቅ.መ.መ. መጋቢ፣ መጋቢነት።
[k] ለ ሉቃ. ፲፱፡፲፭–፳፯።

ጋቢነቱን ሐመግለጫ እንዲያቀርብ በጌታ ይጠበቅበታልና።

፬ በጊዜ ታማኝ እና ሠብልህ የሆነው ለእርሱ በአባቴ የተዘጋጁትን ሀመኖሪያዎች ለመውረስ ብቁ ሆኑ ይገኛል።

፭ እውነት እላችኋለሁ፣ በቤተክርስቲያኗ በዚህ ሠየወይን ስፍራ ውስጥ ያሉ ሽማግሌዎች የመጋቢነታቸውን መግለጫ በዚህ የወይን ስፍራዬ በእኔ ለሚመረጠው ኤጲስ ቆጶሱ ይስጡ።

፮ እነዚህ ነገሮችም፣ በፅዮን ላለው ኤጲስ ቆጶሱ ተላልፈው እንዲሰጡ በመመዝገቢያው ውስጥ ይሁኑ።

፯ እናም ሠየኤጲስ ቆጶሱ ሀላፊነት በተሰጡት ትእዛዛት እና በጉባኤ ድምጽ እንዲታወቅ ይደረጋል።

፰ እናም አሁን፣ እውነት እላችኋለሁ፣ በዚህ ሀይል የሚመረጠው እና የሚሾመው ሰው አገልጋዬ ሠኒወል ኬ ውትኒ ነው። ይህም፣ የቤዛችሁ፣ የጌታ አምላካችሁ ፈቃድ ነው። እንዲህም ይሁን። አሜን።

፱ ከተሰጠው ህግ በተጨማሪ፣ በዚህ የወይን ስፍራ ቤተክርስቲያን ውስጥ የተሾመውን የኤጲስ ቆጶሱን ሀላፊነት የሚያሳውቀው የጌታ ቃል፣ በእውነትም ይህ ነው—

፲ የጌታን ሠንተራ መጠበቅ፤ በዚህ የወይን ስፍራ ቤተክርስቲያን ውስጥ ገንዘቦችን መቀበል ነው፤

፲፩ አስቀድሞ እንደታዘዘው የሽማግሌዎችን መግለጫ ለመቀበል፤ እናም የሚከፍሉት እስካላቸው ድረስ፣ ለሚቀበሉት የሚከፍሉትን እንደፍላጎታቸው ሠለማስተዳደር ነው፤

፲፪ ይህም ደግሞ ለቤተክርስቲያኗ ጥቅም፣ ለድህው እና ለችግረኛው፣ ይቀደስ ዘንድ ነው።

፲፫ እናም ለመክፈል ችሎታ ሠየሌለው ለእርሱ፣ መግለጫው ይወሰድ እናም፣ ጌታ በእጆቹ ከሚያስቀምጣቸው ገንዘቦች እዳውን ለሚከፍልለት፣ ለፅዮን ኤጲስ ቆጶስ ይሰጥ።

፲፬ እናም በመንፈሳዊ ነገሮች፣ ወንጌሉን እና የመንግስቱን ጉዳዮች ለቤተክርስቲያኗ እና ለአለም በማስተዳደር የሚያገለግለውም ታማኝ አገልጋይ፣ እዳውን ለፅዮን ኤጲስ ቆጶስ በዚህ ይከፍላል፤

፲፭ በመሆኑም ከቤተክርስቲያኑ ይወጣል፣ ሠበህጉ መሰረት ወደ ፅዮን የሚመጣው እያንዳንዱ ሰው በፅዮን ኤጲስ ቆጶስ ፊት ሁሉንም ነገሮች ማቅረብ ይኖርበታልና።

፲፮ እናም አሁን፣ እውነት እላችኋለሁ፣ በዚህ የወይን ስፍራ ያሉት እያንዳንዱ ሽማግሌዎች በዚህ የወይን ስፍራ ለሚገኘው ኤጲስ ቆጶስ የሀላፊነቱን መግለጫ መስጠት ይኖርበታል—

፲፯ ከዚህ የወይን ስፍራ ዳኛ ወይም ኤጲስ ቆጶስ በፅዮን ባለ ኤጲስ ቆጶስ የሚሰጥ ሠየምስክር ወረቀት እያንዳንዱን ሰው ተቀባይ ያደርገዋል፣ እናም ለሁሉም ነገሮች መልስ ይሰጣል፣ እንደ ብልህ ሀመጋቢ እና ታማኝ አገልጋይም ያስቆጥረዋል፤

፲፰ አለበለዚያም በፅዮን ኤጲስ ቆጶስ ተቀባይነትን አያገኝም።

፲፱ እናም አሁን፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ለዚህ የወይን ስፍራ ቤተክርስቲያን ኤጲስ ቆጶስ መግለጫ የሚሰጥ እያንዳንዱ ሽማግሌ፣ ለራሱ እና ለመግለጫው በሁሉም ነገሮች ማረጋገጫ ይሆንለት ዘንድ እንዲያቀርብ፣ ባገለገለባት ቤተክርስቲያን ወይም ለቤተክርስቲያናቱ ብቁ ስለመሆኑ ምስክር ይሰጥ።

፲ሐ ት. እና ቃ. ፵፪፡ ፵፪፤ ፲፩፡ ፲፩–፲፫።
፲ሀ ማቴ. ፳፭፡ ፵፭–፵፮።
ለ ት. እና ቃ. ፶፱፡ ፪።
፲ሁ ሀ ቅ.መ.መ. የጌታ የወይን አትክልት ስፍራ።
፲ሂ ሀ ት. እና ቃ. ፵፪፡ ፵፩፤ ፵፯፡ ፳፯፤ ፶፮፡ ፲፯–፲፰፤ ፲፱፡ ፹፤ ፹፫–፹፰።
፲ሃ ሀ ቅ.መ.መ. ዊትኒ፣ ኒውል ኬ።
፲ሄ ሀ ት. እና ቃ. ፫፡ ፯–፲፩፤ ፫፰፡ ፫።
ቅ.መ.መ. ኅተራ።
፲ፀ ሀ ት. እና ቃ. ፫፭፡ ፳፩።
፲ፁ ሀ ቅ.መ.መ. ደሀ።
፲ፂ ሀ ት. እና ቃ. ፵፪፡ ፴–፴፩። ቅ.መ.መ. መቀደስ፣ የቅድስና ህግ።
፲ፃ ሀ ት. እና ቃ. ፭፡ ፳፱፣ ፹፱።
ለ ት. እና ቃ. ፵፪፡ ፴፪።

፳ እና ደግሞም፣ ᎏየተጻፉትን ነገሮችን በመመልከት ሀላፊነት የተሰጣቸው አገ ልጋዮቼም ከኤጲስ ቆጶስ ወይም ከኤጲስ ቆጶሳት በሁሉም ነገሮች እርዳታ የማግኘት መብት አላቸው—

፳፩ ያም ᎏራዕዮችም እንዲታተሙ፣ እናም እስከ ምድር ዳርቻ እንዲሄዱ፤ ቤተ ክርስቲያኗን በሁሉም ነገሮች የሚረዱትን ገንዘቦች ያገኙ ዘንድ፤

፳፪ በሁሉም ነገሮች ራሳቸውን ተቀባይ እንዲያደርጉ፣ እናም እንደ ብልህ መጋ ቢም ይረጋገጥላቸው ዘንድ ነው።

፳፫ እናም አሁን፣ እነሆ፣ ይህም፣ በተ መሰረተችበት በማንኛውም ምድር ውስጥ፣ ለቤተክርስቲያኔ ቅርንጫፎች ሁሉ ምሳሌ ይሆናል። እናም አሁን፣ የምለውን አበቃ ለሁ። አሜን።

፳፬ ስለቤተክርስቲያኗ አባላት፣ ከመንግ ስት ህግጋት በተጨማሪም ጥቂት ቃላት— በመንፈስ ቅዱስ ወደ ፅዮን እንዲሄዱ ᎏየተ መደቡት፣ እናም ወደ ፅዮን ለመጓዝ እድ ለኛም የሆኑት—

፳፭ ከቤተክርስቲያኗ ሶስት ሽማግሌዎች፣ ወይም ከኤጲስ ቆጶስ የምስክር ወረቀትን፣ ለኤጲስ ቆጶሱ ይውሰዱ፤

፳፮ አለበለዚያም ወደ ፅዮን ምድር የሚሄደውም እንደ ብልህ መጋቢ አይረ ጋገጥለትም። ይህም ደግሞ ምሳሌ ነው። አሜን።

ክፍል ፷፫

በጥር ፲፣ ፲፰፻፴፪ (እ.አ.አ.)፣ በሀይረም ኦሀዮ ውስጥ፣ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ እና ለስድኒ ሪግደን የተሰጠ ራዕይ። ካለፈው ህዳር መጀመሪያ ጀምሮ፣ ነቢዩ እና ስድኒ ሪግደን በመስበክ ተጠምደው ነበር፣ እናም በዚህም የተነሳ በቤተክርስቲ ያኗ ላይ ተነስቶ የነበረውን ጥላቻ ለመቀነስ ብዙ ነገሮችን አከናውነው ነበር (የክ ፍል ፷፭ ርዕስን ተመልከቱ)

፩–፪፣ ሽማግሌዎች በመስበክ ይቀጥሉ፤ ፫–፮፣ ጆሴፍ ስሚዝ እና ስድኒ ሪግደን መፅሀፍ ቅዱስ እስኪገባደድ ድረስ መተ ርጎምን ይቀጥሉ።

፩ በእውነትም ጌታ እንዲህ ይላልና፣ እስከ ጉባኤ ድረስ ወንጌሌን በመስበክ፣ እናም በአካባቢው ዙሪያ የሚገኙትን ቤተክርስ ቲያኖችን በማበረታታት ᎏይቀጥሉ ዘንድ ፍቃዴ ነው፤

፪ እና ከዚያም፣ እነሆ፣ በጉባኤው ᎏድምፅ የተለያዩት ተልዕኮአቸው ምን እንደሆኑም ይገለፅላቸዋል።

፫ አሁንም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ አገል ጋዮቼ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ እና ስድኒ ሪግ ደን፣ ጌታም እንዲህ ይላል፣ ዳግም ᎏመተ ርጎም Ꮎየሚያስፈልግበት ጊዜ ነው፤

፬ እናም፣ በተቻለ መጠን፣ እስከ ጉባኤው ድረስም በአካባቢው ዙሪያ ውስጥ ስበኩ፤ እናም ከዚያም ይህም እስኪገባደድ ድረስ የትርጉምን ስራ መቀጠላችሁ አስፈላጊ ነው።

፳ ᎏ ት. እና ቃ. ፷፡፫–፭።
፳፩ ᎏ ቅ.መ.መ. ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች።
፳፩ ᎏ ቅ.መ.መ. ጥሪ፣ በእግዚአብሔር መጠራት፣ የተጠራበት።
፷፫ ፩ ᎏ ይህም በሚስዮን ላይ ያሉት ማለት ነው፤ ት. እና ቃ. ፶፭–፶፮ ተመልከቱ።
፪ ᎏ ት. እና ቃ. ፳፡፳፫።
፫ ᎏ ት. እና ቃ. ፶፭፡፳–፳፩፤ ፷፯፡፲፭። ቅ.መ.መ. የጆሴፍ ስሚዝ ትርጉም (ጆ.ስ.ት.)።
ለ ይህም ጆሴፍ እና ስድኒ ከዚህ በፊት መፅሐፍ ቅዱስን መተርጎም እንዲያቆሙና ወንጌልን እንዲሰብኩ ታዘው ነበር ማለት ነው። ት. እና ቃ. ፷፭፡፪።

፩ እናም ተጨማሪ እውቀቶች እስከሚሰጣቸው ድረስ፣ እንዲሁም እንደተጻፈው፣ ይህም ለሽማግሌዎች ምሳሌ ይሁን።

፪ አሁን ምንም ተጨማሪ በዚህ ጊዜ አልሰጣችሁም። ወገባችሁን ᵐታጠቁ እናም በመጠን ኑሩ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፳፬

በ፲፰፻፳፭ (እ.አ.አ.)፣ በዊይን አውራጃ፣ ኒው ዮርክ፣ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተሰጠ ራዕይ። ቤተክርስቲያኗ ከመደራጀቷ በፊትም፣ ነቢዮ ስለ ርዕሱ መልስ እንዲፈልግ ያደረጉ ስለትክክለኛው የጥምቀት መንገድ ጥያቄዎች ነበሩ። የጆሴፍ ስሚዝ ታሪክ እንደሚገልጸው፣ ይህ ራዕይ የህጻናት ጥምቀት ተቀባይነትን ለማሳየት ሁልጊዜም የሚጠቀሙበትን የቅዱሳት መጻህፍት ጥቅሶች፣ ፩ ቆሮንቶስ ፯፡፲፬ን የሚያብራራ ነው።

፩–፫፣ ጳውሎስ በጊዜው የነበረችውን ቤተክርስቲያን የሙሴን ህግጋትን እንዳታከብር መከረ፤ ፪–፯፣ ህጻናት ልጆች ቅዱስ ናቸው እናም በኃጢአት ክፍያውም የተቀደሱ ናቸው።

፩ ᵐያላመነ ባል በሚስቱ ተቀድሶአልና፥ ያላመነችም ሚስት በባልዋ ተቀድሳለች፤ አለዚያ ልጆቻችሁ ርኵሳን በሆኑ ነበር፤ አሁን ግን የተቀደሱ ናቸው።

፪ አሁን፣ በሐዋርያት ዘመን የግርዘት ህግ በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በማያምኑት አይሁዶች ዘንድ ይተገበር ነበር።

፫ እናም እንዲህ ሆነ በህዝብም መካከል የግርዘት ህግን የሚመለከት ታላቅ ᵐክርክር ተነስቶ ነበር፣ ያላመነ ባል ልጆቹ ᶮእንዲገረዙ እና ተፈጽሞ ለነበረውም ለሙሴ ᵒህግ ተገዢ እንዲሆን ፍላጎት ነበረውና።

፬ እናም እንዲህም ሆነ፣ ልጆቹም በሙሴ ህግ ተገዢ ሆነው በማደጋቸው፣ የአባቶቻቸውን ᵐባህሎች ተከተሉ እናም በክርስቶስም ወንጌል አላመኑም፣ በዚህም ያልተቀደሱ ሆኑ።

፭ ስለዚህ፣ በዚህም ምክንያት ነው ሐዋሪያው ለቤተክርስቲያኗ ከጌታ ሳይሆን ከራሱ፣ በመካከላቸው የሙሴ ᵐህግ ካልተሻረ በስተቀር የሚያምኑ ከማያምኑ ጋር ᶮአንድነት የላቸውምበማለት የጻፈው፣

፮ ልጆቻቸው እንዳይገረዙ፤ እና ይህም በአይሁዶች መካከል ይተገበር ስለነበር፣ ህጻናት ልጆች አይጸደቁም የሚለው ባህልም እንዲቀር የትእዛዝን ፅሑፍ ሰጣቸው፤

፯ ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ᵐየኃጢአት ክፍያ አማካይነት ᶮስለተቀደሱ ህጻናት ᵒልጆች ᵖየተቀደሱ ናቸው፤ እና ይህም የቅዱሳት መጻህፍት ትርጉም ነው።

ክፍል ፳፭

በጥር ፳፭፣ ፲፰፻፳፭ (እ.አ.አ.)፣ በአምኸርስት ኦሀዮ ውስጥ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ

፩ *ሀ* ፩ ጴጥ. ፩፡፲፫።
፳፬ ፩ *ሀ* ፩ ቆሮ. ፯፡፲፬–፲፱።
፫ *ሀ* የሐዋ. ፲፭፡፩–፴፭፤ ገላ. ፪፡፩–፭።
ለ ቅ.መ.መ. መግረዝ።
ሐ ቅ.መ.መ. የሙሴ ህግ።
፱ *ሀ* ቅ.መ.መ. ባህል።
፭ *ሀ* ፪ ኔፊ ፳፭፡፳፩–፳፯።
ለ ቅ.መ.መ. ጋብቻ፣ መጋባት—በሀይማኖቶች መካከል መጋባት።
፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ።
ለ ቅ.መ.መ. ቅዱስ።
ሐ ሞሮኒ ፰፡፰–፲፭፤ ት.እና ቃ. ፳፱፡፴፯–፴፯፤ ፲፱፡፲፡፲።
መ ቅ.መ.መ. ደህንነት—የልጆች ደህንነት።

በኩል የተሰጠ ራዕይ። ይህ ክፍል በአንድ ቀን የተሰጡ ሁለት የተለያዩ ራዕዮችን (የመጀመሪያው ከቁጥር ፩ እስከ ፳፪ ውስጥ እና ሁለተኛው ከቁጥር ፳፫ እስከ ፴፮ ውስጥ ያሉትን) የያዘ ነው። ጊዜውም ጆሴፍ ስሚዝ እንደ ታላቅ ክህነት ፕሬዘደንት ተደግፎ የተሾመበት ጉባኤ ነበር። መልእክታቸውን ሰዎች እንዲገባቸው በሚያደርጉበት ጊዜ ችግር ያጋጠማቸው አንዳንድ ሽማግሌዎች ወዲያውኑ ስለ ሀላፊነታቸው በዝርዝር ለመማር ፍላጎት አደረባቸው። እነዚህ ራዕዮች ተከትለው መጡ።

፩–፭፣ ወንጌልን የሚሰብኩ ታማኝ ሽማግሌዎች ዘለአለማዊ ህይወትን ያገኛሉ፤ ፮–፲፪፣ ሁሉንም ነገሮች የሚያስተምረውን አፅናኙን ለመቀበል ጸልዩ፣ ፲፫–፳፪፣ መልእክታቸውን በማይቀበሉት ላይ ሽማግሌዎች በፍርድ ይቀመጣሉ፤ ፳፫–፴፮፣ የሚስዮኖች ቤተሰቦች ከቤተክርስቲያና እርዳታን ይቀበሉ።

፩ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ እኔ፣ እንዲሁም [1]አልፋና ኦሜጋ፣ ጌታችሁ እና አምላካችሁ፣ በመንፈስ [2]ድምፅም እናገራለሁ—

፪ እናንተ ወንጌሌን ለመስበክ፣ እና [3]የወይን ስፍራዬን [4]ለመግረዝ ስማችሁን የሰጣችሁ ሆይ፣ አድምጡ።

፫ እነሆ፣ እንዲህ እላችኋለሁ ሳትዘገዩ፣ ወይም [5]ስራ ሳትፈቱ፣ በአቅማችሁ ሁሉ እየሰራችሁ ትሄዱ ዘንድ ፍቃዴ ነው—

፬ በሰጠኋችሁ ራዕዮች እና ትእዛዛት መሰረት [6]እውነትን [7]በማወጅ ድምጻችሁን እንደ መለከት ድምጽ ከፍ አድርጉ።

፭ እናም ታማኝ ብትሆኑ ብዙ [8]ነዶም በጀርባችሁ ትሸክማላችሁ፣ እናም [9]በክብር፣ እናም [10]በግርማ፣ [11]አለሟችነት፣ እናም [12]በዘለአለም ሕይወት [13]አክሊልም ይጫን ላችኋል።

፮ ስለዚህ፣ ለአገልጋዬ ዊልያም መክለለን በእውነትም እለዋለሁ፣ ወደ ምስራቅ አገሮች እንዲሄድ የሰጠሁትን ትእዛዝ [14]ሽሬ ዋለሁ፤

፯ እናም አዲስ ተልዕኮ እና አዲስ ትእዛዝንም እሰጠዋለሁ፣ በዚህም እኔ ጌታ ለልቡ [15]ስለማጉረምረሙም [16]እገስጸዋለሁ፤

፰ እናም ኃጢአትን ሰርቷል፤ ይሁን እንጂ፣ ይቅርታ ሰጥቼዋለሁ እና ዳግም እንዲህም እለዋለሁ፣ ወደ ደቡብ አገሮች ሂድ።

፱ እናም አገልጋዬ ሉክ ጆንሰን ከእርሱም ጋር ይሂድ፣ እናም ያዘዝኳቸውን ነገሮችንም ያውጁ—

፲ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉንም ነገሮች የሚያስተምራቸውን [17]አፅናኙን በጌታ ስም በመጥራትም—

፲፩ እንዳይታክቱም ዘወትር [18]ይጸልዩ፤ እና ይህን እስካደረጉ ድረስ፣ እስከመጨረሻም አብሬአቸው እሆናለሁ።

፲፪ እነሆ፣ ይህም እናንተን በተመልከተ የጌታ አምላካችሁ ፈቃድ ነው። እንዲሁም ይሁን። አሜን።

፲፫ እናም ዳግም፣ በእውነት ጌታ እንዲህ ይላል፣ አገልጋዬ [19]ኦርሰን ሀይድ እና አገልጋዬ [20]ሳሙኤል ኤች ስሚዝ ወደ ምስራቅ አገሮች ጎዞአቸውን ይጀምሩ፣ እናም ያዘዝኳቸውን ነገሮች ያውጁ፤ እናም ታማኝም

---

[1] ፩ ሀ ራዕ. ፩፡፰። ቅ.መ.መ. አልፋ እና ኦሜጋ።
[2] ለ ቅ.መ.መ. ራዕይ።
[3] ፪ ሀ ቅ.መ.መ. የጌታ የወይን አትክልት ስፍራ።
[4] ለ ያዕቆ. ፭፡፷፪።
[5] ፫ ሀ ቅ.መ.መ. ስራ ሰልቺ፣ ስራ ፈቺ።
[6] ፬ ሀ ት. እና ቃ. ፲፱፡፴፯።
[7] ለ ቅ.መ.መ. የሚስዮን ስራ።
[8] ፭ ሀ መዝ. ፻፳፮፡፮፣ አልማ ፳፯፡፭።
[9] ለ ቅ.መ.መ. ክብር።
[10] ሐ ቅ.መ.መ. ክብር።
[11] መ ቅ.መ.መ. የማይሞት፣ አለሟችነት።
[12] ሠ ቅ.መ.መ. የዘለዓለም ህይወት።
[13] ረ ቅ.መ.መ. አክሊል።
[14] ፮ ሀ ት. እና ቃ. ፳፮፡፲።
[15] ፯ ሀ ቅ.መ.መ. ሀሳቦች፣ ማጉረምረም።
[16] ለ ቅ.መ.መ. መገሰጽ፣ ተግሳጽ።
[17] ፲ ሀ ዮሐ. ፲፬፡፳፮። ቅ.መ.መ. አፅናኝ።
[18] ፲፩ ሀ ፪ ኔፊ ፴፪፡፱።
[19] ፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. ሀይድ፣ ኦርሰን።
[20] ለ ቅ.መ.መ. ስሚዝ፣ ሳሙኤል ኤች።

ቢሆኑ፣ እስከ መጨረሻም ሐአብሬአቸው እሆናለሁ።

፲፬ እና ደግሞም፣ በእውነት ለአገልጋዬ ላይመን ጆንሰን፣ እናም ለአገልጋዬ ሠኦርሰን ጥራት ይህን እላቸዋለሁ፣ እነርሱም ወደ ምስራቅ አገሮች ጎዞአቸውን ያቅኑ፣ እናም እነሆ፣ እስከ መጨረሻውም እኔ ከእነርሱ ጋር ነኝና።

፲፭ እና ደግሞም፣ ለአገልጋዬ አሳ ዶድስ፣ እና ለአገልጋዬ ካልቭስ ውልሰን እናገራለሁ፣ እነርሱም ወደ ምእራብ አገሮች ጎዞአቸውን ያቅኑ፣ እናም እንዳዘዝኳቸው ወንጌሌን ያውጁ።

፲፮ እናም ታማኝ የሆነውም ሁሉንም ነገሮች ያሸንፋል፣ እናም በመጨረሻም ቀን ሠከፍ ይደረጋል።

፲፯ እና ደግሞም፣ ለአገልጋዬ ሜጀር ኤን አሽሊ እና ለአገልጋዬ በር ሪግስ እላቸዋል ለሁ፣ ወደ ደቡብ አገሮችም ጉዞአቸውን ያቅኑ።

፲፰ አዎን፣ ሁሉም እንዳዘዝኳቸው፣ በየ ቤቱ፣ እና በየመንደሩ፣ እና በየከተማው ይጓዙ።

፲፱ እናም በሚገቡበትም ቤት ውስጥ፣ እና ከተቀበሏችሁም፣ በቤቱ ላይ በረከታ ችሁን ተዉ።

፳ እናም በምትገቡበትም ቤት ውስጥ፣ ባይቀበሏችሁም፣ በቶሎ ከቤቱ ውጡ፣ እናም ምስክር እንዲሆንባቸው ከእግራ ችሁ ትቢያን ሠአራግፉ።

፳፩ እናም ሠበደስታ እና በስኬታማነት ይሞላሉ፤ እናም ይህን እወቁ፣ ፦በፍርድም ቀን የእዚያ ቤት ፈራጆች ትሆናላችሁ እናም ትኮንናቸዋላችሁም፤

፳፪ እናም ከዚያ ቤት ይልቅ ለአረመኔው በፍርድ ቀን ይቀልለታል፤ ስለዚህ፣ ወገባ ችሁን ሠታጠቁ እናም ታማኝ ሁኑ፣ እናም ሁሉንም ነገሮች ታሸንፋላችሁ፣ እናም በመጨረሻም ቀን ከፍ ትደረጋላችሁ። እን ዲህም ይሁን። አሜን።

፳፫ ደግሞም፣ ጌታ ለእናንተ እንዲህ ይላል፣ ስለእናንተ ያለውን ፈቃዱን ለማ ወቅ ስማችሁን የሰጣችሁ የቤተክርስቲያኔ ሽማግሌዎች ሆይ—

፳፬ እነሆ፣ እላችኋለሁ፣ እነዚያን ቤተ ሰቦች መርዳት፣ እናም የተጠሩት እና ወደ አለም ወንጌልን ለመስበክ መሄድ ያለባቸ ውን ቤተሰቦች መርዳት፣ የቤተክርስቲያኗ ሀላፊነት ነው።

፳፭ ስለዚህ፣ እኔ ጌታ ይህን ትእዛዝ እሰ ጣችኋለሁ፣ ወንድሞቻችሁ ልቦቻቸውን ለመክፈት ፈቃደኛ እስከሆኑ ድረስ፣ ለቤ ተሰቦቻችሁ ስፍራዎችን ተቀበሉ።

፳፮ እናም ስፍራዎችን፣ እና የቤተክር ስቲያኗን እርዳታ ለቤተሰባቸው ለመቀ በል የሚችሉት እንደነዚህ አይነቶች፣ ወደ አለም፣ ወደ ምስራቅም ወይም ምዕራብ፣ ወይም ሰሜን፣ ወይም ወደ ደቡብ፣ ከመ ሄድ እንዳይቀሩ።

፳፯ ይጠይቁ እናም ይቀበላሉ፣ ያንኳኩ እናም ይከፈትላቸዋል፣ እናም ከላይም፣ እንዲሁም ሠከአፅናኙ ዘንድ፣ የት መሄድ እንዳለባቸው ያውቃሉ።

፳፰ እና ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ሠቤተሰቡን ፦የማስተዳደር ሀላፊነት ያለበት እያንዳንዱም ሰው፣ ያስተዳድር፣ እናም ዘውዱን በምንም አያጣውም፣ እናም በቤ ተክርስቲያኗም ውስጥ ያገልግል።

፳፱ እያንዳንዱም ሰው በሁሉም ነገሮች ሠይትጋ። እናም ፦ስራ ፈት የሆነ፣ ንስሀ ካል ገባ እና መንገዱን ካላሻሻለ፣ በቤተክርስቲ ያኗ ውስጥ ስፍራ አይኖረውም።

፲፫ሐ ማቴ. ፳፰፡፲፱–፳።
፲፬ ሀ ቅ.መ.መ. ጥራት፣ ኦርሰን።
፲፮ ሀ ት. እና ቃ. ፭፡ ፴፭።
፳ ሀ ማቴ. ፲፡ ፲፬፣
ሉቃ. ፲፡ ፲፩–፲፪፣
ት. እና ቃ. ፳፬፡ ፲፭፣
፳፡ ፲፭።
፳፩ ሀ ማቴ. ፭፡ ፲፩–፲፪።
ለ ቅ.መ.መ. ዳኛ፣ ፍርድ።
፳፪ ሀ ኤፌ. ፮፡ ፲፬፣
ት. እና ቃ. ፳፯፡ ፲፭–፲፰።
፳፯ ሀ ፪ ኔፊ ፴፪፡ ፭፣
ት. እና ቃ. ፳፡ ፪።
ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
፳፰ ሀ ቅ.መ.መ. ቤተሰብ።
ለ ፩ ጢሞ. ፭፡ ፰፣
ት. እና ቃ. ፹፫፡ ፪።
፳፱ ሀ ቅ.መ.መ. ትጋት።
ለ ቅ.መ.መ. ስራ ሰልቺ፣
ስራ ፈቺ።

፴ ስለዚህ፣ አገልጋዬ ስሚኦን ካርተር እና
አገልጋዬ ኢመር ሀሪስ በአገልግሎት ይተ
ባበሩ፤
፴፩ እና ደግሞም አገልጋዬ ኤዝራ ታየር
እና አገልጋዬ [ሀ]ቶማስ ቢ ማርሽም፤
፴፪ እና ደግሞም አገልጋዬ ሀይረም ስሚዝ
እና አገልጋዬ ሬይኖልድ ካሁንም፤
፴፫ እና ደግሞም አገልጋዬ ዳንኤል ስታ
ተን እና አገልጋዬ ሲሞር ብረንሰንም፤
፴፬ እና ደግሞም አገልጋዬ ሲልቨስተር
ስሚዝ እና አገልጋዬ ጊድየን ካርተር
፴፭ እና ደግሞም አገልጋዬ ራግልስ ኤምስ
እና አገልጋዬ ስቲቨን ባርነትም፤
፴፮ እና ደግሞም አገልጋዬ ማይካ ቢ ዌል
ተን እና አገልጋዬ ኢድን ስሚዝም። እንዲ
ህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፷፮

በየካቲት ፲፮፣ ፲፰፻፴፪ (እ.አ.አ.) በሀይረም ኦሀዮ ውስጥ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ እና ለስድኒ ሪግደን የተሰጠ ራዕይ። ከዚህ ራዕይ ጽሑፉ አስቀድሞ፣ የጆሴፍ ስሚዝ ታሪክ እንደሚገልጸው፥ "ከአምኸርስት ጉባኤ እንደተመለስኩ፣ ቅዱሳን መጻህ ፍትን መተርጎምን ቀጠልኩ። ከተቀበልኳቸው ከተለያዩ ራዕዮች፣ የሰውን ልጅ ደህንነት የሚመለከቱ ብዙ አስፈላጊ ነጥቦች ከመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተወ ሰዱ፣ ወይም ከመከማቸቱ በፊት እንደጠፉ ግልፅ ነበር። እግዚአብሔር ለእያን ዳንዱ በስጋ ባከናወነው በኩል ደመወዙን የሚሰጥ ከሆነ፣ ለቅዱሳን የዘለአለም ቤት እንዲሆን የተወሰነበት ሰማይ ከአንድ በላይ የሆኑ መንግስታትን እንደሚያ ጠቃልል ቀሪው እውነት በራሱ የሚያስረዳ ነው። በዚህም መሰረት፣ . . . የቅዱስ ዮሐንስን ወንጌል ስንተረጉም፣ እኔ እና ሽማግሌ ሪግደን የሚቀጥለውን ራዕይ ተመለከትን።" ራዕዩ በተሰጠበት ግዜ፣ ነቢዩ ዮሐንስ ፭፡፳፱ን እየተረጎመ ነበር።

፩–፬፣ ጌታ እግዚአብሔር ነው፤ ፭–፲፣ የመንግስት ሚስጥራት ለታማኞቹ ሁሉ ይገለጣሉ፤ ፲፩–፲፮፣ ሁሉም በጻድቃንም ሆነ በኃጢአተኛ ትንሳኤ ከሞት ይነሳሉ፤ ፲፯–፳፬፣ የብዙ አለማት ኗሪዎች በኢየ ሱስ ክርስቶስ የኃጢአት ክፍያ አማካይነት የእግዚአብሔር ወንዶች እና ሴቶች ልጆች ናቸው፤ ፳፭–፳፱፣ የእግዚአብሔር መል አክ ተጣለ እናም ዲያብሎስም ሆነ፤ ፴–፴፱፣ የጥፋት ልጆችም በዘለአለም እርግ ማን ይሰቃያሉ፤ ሌሎች ሁሉም የተወሰነ የደህንነትን ደረጃ ያገኛሉ፤ ፣–፷፣ በሰለ ስቲያል መንግስት ውስጥ ዘለአለማዊ ክብር ያላቸው ፍጡራን ክብር እና ደመወዝ ተገ ልጿል፤ ፷፩–፷፡ የተረስትሪያልን መን ግስት የሚወርሱትም ተገልጸዋል፤ ፷፡–፷፣ በቲለስቲያል፣ ተረስትሪያል፣ እና በሰለስቲያል ክብሮች ውስጥ ያሉት ሁኔ ታቸው ተገልጿዋል፤ ፷፣–፷፣ ታማኝ የሆኑት የእግዚአብሔርን መንግስት ሚስ ጥራት በመንፈስ ቅዱስ ሀይል አማካይነት ማየት እና መረዳት ይችላሉ።

፩ [ሀ]አድምጡ፣ እናንት ሰማያት ሆይ፣
ምድር ሆይ ጆሮሽን ስጪ፣ እናም ነዋሪ
ዎችዋም ተደሰቱ፣ ጌታ [ለ]እግዚአብሔር
ነውና፣ እናም ከእርሱም በቀር [ሐ]ማንም
[መ]አዳኝ የለምና።

፴፩ ሀ ቅ.መ.መ. ማርሽ፣ ቶማስ ቢ.
፴፭ ሀ ኢሳ. ፩፡፪።
ለ ኤር. ፲፡፲።
ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ—እግዚአብሔር ወልድ።
ሐ ኢሳ. ፵፣፡፲፩፣ ሆሴ. ፲፣፡፱።
መ ቅ.መ.መ. አዳኝ።

፪ ጥበቡ ᐟታላቅ ነው፣ መንገዶቹም ᐠድንቅ ናቸው፣ እናም የአሰራሩንም መጠን ማንም ሊያገኘው አይቻለውም።

፫ ᐟአላማዎቹ አይወድቁም፣ እጁንም ይከለክል ዘንድ የሚቻለው ማንም የለም።

፬ ከዘለአለም እስከ ዘለአለም ᐟአንድ ነው፣ እና አመታቱም ከቶ ᐠአያልቁም።

፭ ጌታ እንዲህ ይላል—እኔ ጌታ ᐟለሚፈሩኝ ᐠመሀሪ እና ይቅር ባይ ነኝ፣ እና በፅድቅ እና በእውነት እስከ መጨረሻው ᐠየሚያገለግሉኝንም በማክበር እደሰታለሁ።

፮ ዋጋቸውም ታላቅ እና ᐟክብራቸውም ዘለአለማዊ ይሆናል።

፯ እና ለእነርሱም ሁሉንም ᐟሚስጥራት፣ አዎን፣ ከጥንት ጀምሮ የተሰወሩትን የመንግስቴን ሚስጥራት ሁሉ ᐠእገልጽላቸዋለሁ፣ እና በሚመጡት ዘመናትም መንግስቴን የተመለከቱትን ነገሮች ሁሉ በጎ ፈቃዴን ያውቁ ዘንድ አደርጋቸዋለሁ።

፰ አዎን፣ የዘለአለምን ድንቆችንም ያውቃሉ፣ የሚመጡትን፣ እንዲሁም የብዙ ትውልዶች ነገሮችንም አሳያቸዋለሁ።

፱ እናም ᐟጥበባቸውም ታላቅ ይሆናል፣ እናም ᐠመረዳታቸውም እስከ ሰማያት የዘለቀ ይሆናል፤ እናም የጥበበኞችም ጥበብ ትጠፋለችና፣ እናም የአስተዋዮችም ᐠማስተዋል ትሰወራለች።

፲ ᐟበመንፈሴም ᐠአብራላቸዋለሁና፣ እናም የፈቃዴን ሚስጥራት—አዎን እንዲሁም ᐠሓሳይን ያላየውን ጆሮም ያልሰማውን፣ በሰውም ልብ ያልታሰቡትንም ነገሮች፣ ᐟበሀይሌ አሳውቃቸዋለሁ።

፲፩ እኛ፣ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ እና ስድኒ ሪግደን፣ በጌታችን አንድ ሺ ስምንት መቶ ሰላሳ ሁለት አመት በየካቲት አስራ ስድስት ቀን ᐟበመንፈስ ሆነን—

፲፪ ᐟበመንፈስ ሀይልም፣ የእግዚአብሔርን ነገሮች ለማየት እና ለመረዳት፣ ᐠአይኖቻችን ተከፈቱ እናም እውቀቶቻችንም ብሩህ ሆኑ—

፲፫ እንዲሁም አለም ከመፈጠሯ በፊት ከመጀመሪያ ጀምሮ የነበሩት ነገሮችም፣ በአብ እቅፍ ውስጥ በነበረው በአንድያ ልጁ በኩል፣ ᐟከመጀመሪያው ጀምሮ፣ በአብ ተቀድሰው የነበሩትም፤

፲፬ ስለ እርሱም ምስክርን እንሰጣለን፤ እናም የምንመሰክረውም፣ ልጅ ስለሆነው፣ ያየነው እናም በሰማያዊ ᐟራዕይ ᐠስላነጋገርነው ስለኢየሱስ ክርስቶስ ሙሉ ወንጌል ነው።

፲፭ ጌታ የሰጠንን ᐟየትርጉም ስራ እየሰራን እያለ፣ እንደሚከተለው ወደ ተሰጠን ወደ ዮሐንስ መፅሐፍ በአምስተኛው ምዕራፍ ቁጥር ሀያ ዘጠኝ ላይ ደረስን—

፲፮ ስለ ሙታን ትንሳኤ፣ እነዚያ ᐟየሰው ልጅ ድምፅ ᐠስለ ሚሰሙት በመናገር፥

፲፯ ᐟመልካምም ያደረጉ ᐠጻድቃን

፪ ᐟ ፪ ኔፊ ፪፡፳፬፤
ት. እና ቃ. ፴፰፡፩–፫።
ለ ራዕ. ፲፭፡፫።
፫ ᐟ ፩ ነገሥ. ፰፡፶፤
ት. እና ቃ. ፩፡፴፤
፳፬፡፩ ፴፩።
፬ ᐟ ዕብ. ፲፫፡፰፤
ት. እና ቃ. ፴፭፡፩፤
፴፰፡፩–፬፤ ፴፱፡፩–፫።
ለ መዝ. ፻፪፡፳፭–፳፯፤
ዕብ. ፩፡፲፪።
፭ ᐟ ዘዳግ. ፮፡፲፫፤
ኢ.ያ. ፀ፡፳፫–፳ፀ።
ቅ.መ.መ. ማክበር፤
ፍርሀት።
ለ ዘፀአ. ፴ፀ፡፮፤
መዝ. ፻፫፡፰።
ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።
ሐ ት. እና ቃ. ፀ፡፪።
፯ ᐟ ቅ.መ.መ. የሰለስቲያል ክብር።
፰ ᐟ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ሚስጥሮች።
ለ ት. እና ቃ. ፵፪፡፳፭፤ ፶፱፡፱፤
፶፳፡፲፪፤ ፻፳፭፡፳፯–፴፫።
፱ ᐟ ቅ.መ.መ. ጥበብ።
ለ ቅ.መ.መ. ማስተዋል።
ሐ ኢሳ. ፳፱፡፲፬፤
፪ ኔፊ ፱፡፳፯–፳፱።
፲ ᐟ ሞሮኒ ፣፡፭።
ለ ቅ.መ.መ. ምስክርነት፤
ራዕይ።
ሐ ኢሳ. ፳፯፡፬፤
፭ ቆሮ. ፪፡፱፤
፫ ኔፊ ፲፯፡፲፭–፲፯፤
ት. እና ቃ. ፳፯፡፻፲ፀ–፻፲፯።
መ ቅ.መ.መ. ሀይል።
፲፩ ᐟ ራዕ. ፩፡፣።
፲፪ ᐟ ቅ.መ.መ. መለወጥ።
ለ ት. እና ቃ. ፻፣፡፩፤ ፻ወ፶፯፡፩፤
፻ወ፶፡፲፩፤ ፳፯ወ፡፱።
፲፫ ᐟ ሙሴ ፀ፡፪።
፲፬ ᐟ ቅ.መ.መ. ራዕይ።
ለ ት. እና ቃ. ፻፱፡፶፯።
፲፭ ᐟ ቅ.መ.መ. የጆሴፍ ስሚዝ ትርጉም (ጆ.ስ.ት.)።
፲፮ ᐟ ቅ.መ.መ. የሰው ልጅ።
ለ ዮሐ. ፭፡፳፭።
፲፯ ᐟ ቅ.መ.መ. ስራዎች።
ለ የሐዋ. ፳ፀ፡፲፭።

ሐትንሣኤ፣ ክፉትንም ያደረጉ በኃጥአን ትንሣኤ ይነሳሉ።

፲፰ አሁን ይህም እንድንደነቅ አደረገን፣ ምክንያቱም በመንፈስ ለእኛ ተሰጥቶን ነበርና።

፲፱ እናም በእነዚህ ነገሮች ላይ ᵐእያሰላሰልን ሳለን፣ ጌታ የመረዳት አይኖቻችንን ነካ እናም ተከፈቱ፣ እናም የጌታ ክብርም በዙሪያችን በራ።

፳ እናም የወልድን ᵐክብር፣ ᵃበአብ ሐቀኝ በኩል ተመለከትን እናም እርሱን በሙላት ተቀበልን፤

፳፩ እናም ቅዱሳን ᵐመላእክት፣ እና በዙፋኑ ፊት ᵃተቀድሰው የነበሩትን፣ እግዚአብሔርን ሲያመልኩት እና እርሱንም ለዘለአለም ሐየሚያመልከውን በጉን አየን።

፳፪ እናም አሁን፣ ስለ እርሱ ከተሰጡት ብዙ ᵐምስክሮች በኋላ፣ ይህም በመጨረሻ ስለ እርሱ የምንሰጠው ምስክርነት፥ እርሱ ᵃህያው መሆኑን ነው!

፳፫ ᵐበእግዚአብሔር ቀኝ ᵃአይተነዋልና፤ እናም እርሱ የአብ ሐአንድያ ልጅ እንደሆነም ሲመሰክርም ድምፅ ሰምተናል—

፳፬ ᵐአለማትም ᵃበእርሱ፣ እናም በእርሱም አማካይነት፣ እናም ከእርሱም ዘንድ ናቸው እናም ተፈጥረዋል፣ እናም ነዋሪዎችዋም የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ሐልጆች ናቸው።

፳፭ እናም ይህንም አየን፣ እንመሰክራለንም፣ በእግዚአብሔር ፊት ስልጣን የነበረው፣ አብ ይወደው የነበረው እና በአብም እቅፍ የነበረው በአንድያ ልጁ ያመጸው፣ የእግዚአብሔር ᵐመልአክ ከእግዚአብሔር እና ከወልድ ፊት ተጥሎ ነበር፣

፳፮ እና የጥፋት ልጅ ተብሎም ተጠራ፣ ሰማያትም ስለእርሱ አነቡ—እርሱም ᵐሉሲፈር፣ የንጋት ልጅ ነበር።

፳፯ እናም የንጋት ልጅ የሆነው እርሱም ᵐየወደቀ ነው፣ ወድቋልም፣ ይህንንም ተመለከትን፣ እናም አስተዋልን!

፳፰ እናም በመንፈስ እያለን፣ ጌታ ራዕይን እንድንፅፍ አዘዘን፤ ሰይጣንን፣ እንዲሁም በእግዚአብሔር ላይ ᵐያመጸውን፣ እና የእግዚአብሔርንና የእርሱን ክርስቶስ መንግስት ለመውሰድ የሻውን የቀደመውን ᵃእባብ ሐዲያብሎስ አይተነዋልና—

፳፱ እነሆ፣ ከእግዚአብሔር ቅዱሳን ጋርም ᵐተዋጋ፣ እናም በዙሪያቸውም ከበባቸው።

፴ እናም በራዕይም የተዋጋቸውን እና ያሸነፋቸውን ስቃይ ተመለከትን፣ እንደ ህም ሲል የጌታ ድምፅ ወደ እኛ መጣ፥

፴፩ ጌታም ሀይሌን ስለሚያውቁት ሁሉ፣ እናም በዚህም ተካፋይ ስለሆኑት፣ እናም በዲያብሎስም ሀይል አማካይነት ራሳቸውን ᵐእንዲሸነፉ እውነትንም እንዲክዱና ሀይሌም እንዲረክስ የፈቀዱትን በተመለከተ እንዲህ ይላል—

፴፪ ባይወለዱ ይሻላቸው ብዬ ያልኳቸው፣ ᵐየጥፋት ᵃልጆች እነርሱ ናቸው፤

፲፯ ሐ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
፲፱ ሀ ቅ.መ.መ. ማሰላሰል።
፳ ሀ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—የክርስቶስ ክብር።
ለ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ—እግዚአብሔር አብ።
ሐ የሐዋ. ፯፡ ፶፮።
፳፩ ሀ ማቴ. ፳፭፡ ፴፩፣ ት. እና ቃ. ፲፡ ፴–፴፣ ፲፮፡ ፴፯።
ለ ቅ.መ.መ. ቅድስና።
ሐ ቅ.መ.መ. ማምለክ።
፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. ምስክርነት።
ለ ት. እና ቃ. ፳፡ ፲፯።
፳፫ ሀ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ—እግዚአብሔር አብ።
ለ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—ክርስቶስ ከሚችነት በኋላ መገለጡ።
ሐ ዮሐ. ፩፡ ፲፱።
ቅ.መ.መ. አንድያ ልጅ።
፳፬ ሀ ሙሴ ፩፡ ፴፭–፴፫፣ ፮፡ ፴።
ቅ.መ.መ. መፍጠር፣ ፍጥረት።
ለ ዕብ. ፩፡ ፩–፫፣ ፫ ኔፊ ፱፡ ፲፭፣ ት. እና ቃ. ፲፱፡ ፱፣ ፻፫፡ ፳–፲።
ሐ የሐዋ. ፲፯፡ ፳፰፣ ፳፱፣ ዕብ. ፲፪፡ ፱።
ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ወንድ እና ሴት ልጆች።
፳፭ ሀ ት. እና ቃ. ፳፱፡ ፴፯–፴፱፣ ሙሴ ፭፡ ፩–፱።
ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
፳፮ ሀ ኢሳ. ፲፬፡ ፲፪–፲፯።
ቅ.መ.መ. አጥቢያ ኮከብ።
፳፯ ሀ ሉቃ. ፲፡ ፲፰።
፳፰ ሀ ቅ.መ.መ. የሰማይ ጦርነት።
ለ ራዕ. ፲፪፡ ፱።
ሐ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
፳፱ ሀ ራዕ. ፲፫፡ ፮፣ ፪ ኔፊ ፪፡ ፲፰፣ ፳፰፡ ፲፱–፳፫።
፴፩ ሀ ቅ.መ.መ. ክህደት።
፴፪ ሀ ት. እና ቃ. ፫፮፡ ፳፮፣ ሙሴ ፭፡ ፳፪–፳፮።
ለ ቅ.መ.መ. የጥፋት ልጆች።

ᏍᏗᏗ ከዲያብሎስ እና ከመላእክቱ ጋር ለዘ
ለአለም በእግዚአብሔር ቁጣ ለመሰቃየት
የተረገሙ የቁጣ እቃዎች ናቸውና፤
ᏍᏗᏘ እነርሱን በተመለከተ በዚህም አለም
ይሁን በሚመጣው አለም ᵐይቅርታ የላቸ
ውም ብያለሁ—
ᏍᏗᏓ ከተቀበሉት በኋላ መንፈስ ቅዱስን፣
እና የአብን አንድያ ልጅ ᵐስለካዱት፣ እናም
እርሱንም በራሳቸው ᵃስለሰቀሉት እና ስላ
ዋረዱት ይቅርታ የላቸውም።
ᏍᏗᏔ እነዚህም፣ ከዲያብሎስ እና ከመላእ
ክቱ ጋር ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ᵐባሕር የሚ
ሄዱት ናቸው—
ᏍᏗᏕ እናም ሁለተኛው ᵐሞትም ሀይልን
የሚያገኝባቸውም እነርሱ ናቸው፤
ᏍᏗᏖ አዎን፣ በእውነትም፣ ከቁጣው ስቃይ
በኋላ፣ በጌታ ዘመንም የማይድኑት እነርሱ
ᵐብቻ ናቸው።
ᏍᏗᏗ ሌሎቹም ሁሉ፣ በታረደው፣ አለማ
ትም ከመሰራታቸው አስቀድሞ በአብ እቅፍ
በነበረው ᵐበበጉ ታላቅ ድል እና ክብር የተ
ነሳ፣ በሙታን ᵃትንሳኤ ᶣይመጣሉ።
ᏍᏘ እና ይህም የሰማያት ድምፅ ለእኛ የመ
ሰከረልን ምስራች ᵐወንጌል ነው—
ᏍᏙ እርሱም፣ እንዲሁም ኢየሱስ፣ ለአ
ለም ᵐሊሰቀልና ᵃየአለም ኃጢአቶችን
ᶣሊሸከም፣ እናም አለምንም ᵐሊቀድ
ስና፣ ከርኩሳትም ᵐᵐሊያጸዳ ወደ አለም
እንደመጣ፣ የሰማያት ድምፅ የመሰከረልን
ምስራች ይህ ነው፤
ᏍᏚ በእርሱም አማካይነት አብ በእርሱ
ሀይል ያደረጋቸውን እና በእርሱ የተሰሩት
ሁሉ ᵐይድኑ ዘንድ፤
ᏍᏚ እርሱም አብን የሚያከብር፣ እናም
አብም ከገለጠው በኋላ ወልድን ከሚክዱት
የጥፋት ልጆች በስተቀር የእጆቹን ስራዎች
ሁሉ የሚያድን ነው።
ᏍᏚ ስለዚህ፣ ከእነርሱም በስተቀር ሁሉን
ያድናል—እነርሱም መጨረሻ ወደሌለው፣
ᵐየዘለአለም ᵃቅጣት ወደሆነው፣ ᶣከዲያ
ብሎስ እና ከመላእክቱ ጋር ገዢ ለመሆን
ስቃያቸው የሆነው ᵐትላቸው ወደ ማይሞ
ትበት እሳቱም ወደ ማይጠፋበት ወደ ዘለ
አለም ቅጣት ይሄዳሉ—
ᏍᏚ እናም ᵐመጨረሻውን፣ ወይም ስፍ
ራውን፣ ወይም ስቃያቸውን ማንም ሰው
አያውቅም፤
ᏍᏚ ይህም አልተገለጠም፣ ወይም የዚህ
ተካፋዮች ከሆኑት በስተቀር፣ ይህም የተ
ገለጠም አይደለም፣ ወይም ለሰውም አይ
ገለጠም፤
ᏍᏚ ይሁን እንጂ፣ እኔ ጌታ ይህን በራዕይ
ለብዙዎች አሳይቻለሁ፣ ነገር ግን ወዲያ
ውም ደግሜ ዘግቼዋለሁ።
ᏍᏚ ስለዚህ፣ የዚህን መጨረሻ፣ ስፋት፣
ከፍታ፣ ᵐጥልቀት፣ እና ስቃይ አልተረዱ
ትም፣ ወይም በዚህ ᵃፍርድ ᶣከተመደቡት
በስተቀር ማንም ሰው አይረዳውም።
ᏍᏚ እናም ድምፅም እንዲህ ሲል ሰማን፥
ይህን ራዕይ ጻፍ፣ የኃጢአተኞችም ስቃይ
መጨረሻ ይህ ነውና።
ᏍᏚ ደግሞም እንመሰክራለን—አይተን

ᏍᏘ ᵐ ማቴ. ᏗᏑ፥ᏍᏕ–ᏍᏑ።
ᵃ ቅ.መ.መ. ይቅርታ ማድረግ።
ᏍᏓ ᵐ ᏑᏭ. ᏑᏎ፥ᏣᏓᏑᏎ፤
ᵃ አለማ ᏍᏘᏗ፥ᏓᏎ።
ᵐ ቅ.መ.መ. ይቅርታ
ᵃ የሌለው ኃጢያት።
ᵃ ዕብ. ᏓᏎ፥ᏘᏎ፤ ᏕᏄᏎ ᏗᏘᏗ፥ᏓᏎ፤
ት. እና ቃ. ᏑᏍᏑᏑ፥ᏣᏓᏎ።
ᏍᏓᏎ ᵐ ራዕ. ᏗᏘᏗ፥ᏣᏗ ᏣᏗ፥ᏗᏗ፤
ᏣᏕᏕ፥ᏣᏗ፤
ᏑᏎ ᏄᏎ ᏘᏗ፥ᏗᏓᏎ ᏣᏣᏗ፥ᏣᏗᏗ፤
አለማ ᏗᏑᏑ፥ᏗᏓᏎ–ᏗᏣᏗ፤
ት. እና ቃ. ᏣᏗᏑ፥ᏗᏓᏎ።
ᏍᏓᏎ ᵐ ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ሞት።
ᏍᏣᏗ ᵐ ቅ.መ.መ. የጥፋት ልጆች።
ᏍᏘᏘ ᵐ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ።
ᵃ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
ᶣ ይህም መቢዝጦት ማለት ነው፤
ቁጥር ᏍᏣᏗ ተመልከቱ።
ሁሉም ከሞት ይነሳሉ።
አለማ ᏗᏕᏗ፥ᏍᏕ–ᏍᏣᏗ
ተመልከቱ።
ᵐ ቅ.መ.መ. ህያው ማድረግ።
ᏍᏚ ᵐ ᏑᏎ ᏄᏎ፥ᏗᏑᏑ–ᏣᏑᏑ።
ᵐ ቅ.መ.መ. ወንጌል፤
የቤዛነት ዕቅድ።
ᏍᏕᏕ ᵐ ቅ.መ.መ. መሰቀል።
ᵃ ᏕᏑ ዮሐ. ᏑᏎ፥ᏕᏑᏎ፤
ᶣ ኢሳ. ᏘᏑᏑ፥ᏑᏑᏑ፤
ዕብ. ᏘᏑ፥ᏣᏣᏣ።
ᵐ ቅ.መ.መ. ቅድስና።
ᵐᵐ ቅ.መ.መ. ቤዛ፣
ማዳን፣ ቤዛነት።
ᏍᏑᏑ ᵐ ቅ.መ.መ. ደህንነት።
ᏍᏘᏘ ᵐ ት. እና ቃ. ᏗᏘᏗ፥ᏎᏗᏑᏑ።
ᵃ ቅ.መ.መ. ኩነኔ።
ᶣ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
ᵐ ኢሳ. ᏣᏎ፥ᏣᏘᏘ፤
ማር. ᏘᏑ፥ᏍᏗᏗ–ᏍᏣᏣ።
ᏍᏣᏗ ᵐ ት. እና ቃ. ᏣᏘᏗ፥ᏣᏣᏗ–ᏣᏘᏗ።
ᏍᏣᏣ ᵐ ራዕ. ᏣᏣ፥ᏕᏘ
ᵃ አለማ ᏍᏘᏑ፥ᏣᏑᏑ።
ᶣ ይህም የፍርድ ውሳኔ
መስጠት፣ መመደብ
ማለት ነው።

ሰምተናልና፣ እናም ይህም መልካምን በማድረግ በጻድቃት [ሀ]ትንሣኤ የሚነሱትን በሚመለከት የክርስቶስ ወንጌል [ለ]ምስክርነት ይህ ነው—

፶፩ እነርሱም የኢየሱስን ምስክር የተቀበሉ፣ እናም በስሙም [ሀ]ያመኑ እና ቀብሩን በሚመስል [ለ]ድርጊት፣ በስሙ በውሀ ውስጥ [ሐ]በመቀበር [መ]የተጠመቁ ናቸው፣ እና ይህንም ያደረጉት እርሱ በሰጣቸው ትእዛዝ መሰረት ነው—

፶፪ ይህም ትእዛዛትን በማክበርም ከኃጢአታቸው ሁሉ [ሀ]እንዲታጠቡ እና [ለ]እንዲጸዱ፣ እናም ወደዚህ [ሐ]ሀይል [መ]በተሾመው እና በተሳሰረው [ሠ]እጆችንም በመጫን መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ በሰጠው ትእዛዝ መሰረት ነው፤

፶፫ እናም በእምነት ያሸነፉም፣ እናም መልካም ለሚያደርጉት እና ለእውነተኞች ሁሉ አብ በሚያፈሰው [ሀ]በቅዱሱ የተስፋ መንፈስ [ለ]ታትመዋል።

፶፬ እነርሱም [ሀ]የበኩር ልጅ ቤተክርስቲያን ናቸው።

፶፭ እነርሱም አብ [ሀ]ሁሉንም ነገሮች በእጆቻቸው የሰጣቸው ናቸው—

፶፮ እነርሱም የእርሱን ሙላት እና ክብር የተቀበሉ [ሀ]ካህናት እና ነገስታት ናቸው፤

፶፯ እናም ከአንድያ ልጅ [ሀ]ስርዓት እና [ለ]የሔኖክ ስርዓት ከነበረው እንደ መልከጼዴቅ ስርዓት የልዑልም [ሐ]ካህናት ናቸው።

፶፰ ስለዚህ፣ እንደተጻፈውም፣ እነርሱ [ሀ]አማልክቶች፣ እነሆ [ለ]የእግዚአብሔር [ሐ]ልጆች ናቸው፣

፶፱ ስለዚህ፣ ሁሉም ነገሮች የእነርሱ ናቸው፣ በህይወትም ይሁን በሞት፣ ወይም አሁን ያሉ ነገሮች ወይም ወደፊት የሚመጡት ነገሮች፣ [ሀ]ሁሉም የእነርሱ ናቸውም እነርሱ የክርስቶስ ናቸው፣ እናም ክርስቶስም የእግዚአብሔር ነው።

፷ እናም እነርሱም ሁሉንም ነገሮች [ሀ]ያሸንፋሉ።

፷፩ ስለዚህ፣ ማንም በሰው [ሀ]አይመካ፣ ነገር ግን ጠላቶቹን ሁሉ ከእግሩ በታች [ለ]በሚያደርገው በእግዚአብሔር [ሐ]ይመካ።

፷፪ እነዚህም በእግዚአብሔር እና በእርሱ ክርስቶስ [ሀ]ፊት ለዘለአለም [ለ]ይኖራሉ።

፷፫ በምድር በህዝቡ ላይ [ሀ]ሊነግስ በሰማይ ደመና [ለ]በሚመጣበት ጊዜ ይዞአቸው የሚመጣውም [ሐ]እነዚህ ናቸው።

፶ ሀ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
ለ ቅ.መ.መ. ምስክርነት።
፶፩ ሀ ት. እና ቃ. ፳፥፳፭–፳፯፣ ፴፯።
ለ ት. እና ቃ. ፻፳፰፥፲፫።
ሐ ሮሜ ፮፥፫–፭።
ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣ መጥመቅ—በማጥለቅ መጥመቅ።
መ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣ መጥመቅ።
፶፪ ሀ ፪ ኔፊ ፱፥፳፫፤ ሞሮኒ ፰፥፳፭–፳፮።
ለ ቅ.መ.መ. ንጹህ፣ ንጹህነት።
ሐ ቅ.መ.መ. ስልጣን።
መ ቅ.መ.መ. መሾም፣ ሹመት።
ሠ ቅ.መ.መ. እጅን መጫን፤ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ።
፶፫ ሀ ኤፌ. ፩፥፲፫፤ ት. እና ቃ. ፻፴፪፥፫–፳።
ቅ.መ.መ. ቅዱስ የተስፋ መንፈስ።
ለ ቅ.መ.መ. ማተም፣ ማስተሳሰር።
፶፬ ሀ ዕብ. ፲፪፥፳፫፤ ት. እና ቃ. ፺፫፥፳፩–፳፪።
ቅ.መ.መ. በኩር።
፶፭ ሀ ፪ ጴጥ. ፩፥፫–፬፤ ት. እና ቃ. ፶፥፳፮–፳፰፤ ፻፬፥፵፭–፵፰።
፶፮ ሀ ዘፀአ. ፲፱፥፮፤ ራዕ. ፩፥፭–፮፤ ፭፥፮።
፶፯ ሀ ት. እና ቃ. ፻፯፥፩–፬።
ለ ዘፍጥ. ፭፥፳፩–፳፬።
ቅ.መ.መ. ሔኖክ።
ሐ ቅ.መ.መ. ካህን፣ የመልከጼዴቅ ክህነት።
፶፰ ሀ መዝ. ፹፪፥፩፣ ፮፤ ዮሐ. ፲፥፴፬–፴፮።
ቅ.መ.መ. ሰው፣ ሰዎች—የሰው እንደ እግዚአብሔር አይነት ለመሆን ያለው ችሎታ።
ለ ት. እና ቃ. ፻፳፩፥፵፪።
ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ።
ሐ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ወንድ እና ሴት ልጆች።
፶፱ ሀ ሉቃ. ፲፪፥፵፪–፵፬፤ ፫ ኔፊ ፳፰፥፲፤ ት. እና ቃ. ፹፬፥፴፮–፴፰።
፷ ሀ ራዕ. ፫፥፭፤ ፳፩፥፯።
፷፩ ሀ ዮሐ. ፭፥፵፩–፵፬፤ ፩ ቆሮ. ፫፥፳፩–፳፫።
ለ ት. እና ቃ. ፵፱፥፮።
ሐ ፪ ኔፊ ፴፫፥፮፤ አልማ ፳፮፥፲፩–፲፮።
ቅ.መ.መ. ክብር።
፷፪ ሀ ት. እና ቃ. ፯፴፥፯።
ቅ.መ.መ. የዘለዓለም ህይወት።
ለ መዝ. ፲፭፥፩–፫፤ ፳፬፥፫–፬፤ ፩ ኔፊ ፲፭፥፴፫–፴፬፤ ሙሴ ፮፥፶፯።
፷፫ ሀ ት. እና ቃ. ፶፰፥፳፪።
ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—የክርስቶስ የአንድ ሺህ አመት ግዛት።
ለ ማቴ. ፳፬፥፴።
ሐ ት. እና ቃ. ፹፰፥፺፯–፺፰።
ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።

፰፤ እነዚህም ᵐበመጀመሪያው ትንሳኤ ስፍራም የሚኖራቸውም እነዚህ ናቸው።

፰፭ እነዚህም በጻድቃን ᵐትንሳኤ የሚመጡት ናቸው።

፰፮ ወደ ᵐፅዮን ᵃተራራ፣ እናም ከሁሉም በላይ ቅዱስ ወደሆነው ሰማያዊ ስፍራ፣ ወደ ህያው እግዚአብሔር ከተማ የሚመጡትም እነዚህ ናቸው።

፰፯ እነዚህም ወደ አእላፋት መላእክት፣ ወደ ᵐሔኖክ እና ወደ ᵃበኩራት ቤተክርስቲያንና ወደ ታላቁ ጉባኤ የመጡት ናቸው።

፰፰ እነዚህም እግዚአብሔር እና ክርስቶስ ሁሉንም ᵐበሚፈርዱበት በሰማይ ስሞ ቻቸው ᵃየተጻፉላቸውም ናቸው።

፰፱ እነዚህ ᵐየአዲስ ኪዳን አማላጅ በሆ ነው፣ ይህን ፍጹም ᵃየኃጢአት ክፍያን በመፈጸም የራሱን ሐደም በማፍሰስ ባከና ወነው በኢየሱስ ᵐፍጹም የሆኑት ጻድቃን ᵐሰዎች ናቸው።

፰ እነዚህ ሰውነታቸው ᵐሰለስቲያል የሆኑ ናቸው፣ ᵃክብራቸውም እንደ ሐጸሀይ፣ እን ዲሁም ከሁሉም በላይ በሆነ የእግዚአብሔር ክብር፣ ክብሩም የጠፈር ጸሀይ አይነተኛ ሆኖ እንደተጻፈ የሆነው ነው።

፰፩ እና ደግሞም፣ ᵐየተረስትሪያልን አለም አየን፣ እና እነሆ እናም አስተውሉ፣ እነዚህም የተረስትሪያል የሆኑ፣ ᵃጨረቃ ከጠፈር ጸሀይ እንደሚለይ፣ ክብራቸው የአብን ሙላት ከተቀበለው የበኩር ቤተ ክርስቲያን የተለዩ ናቸው።

፰፪ እነሆ፣ እነዚህም ᵐካለህግ የሞቱት ናቸው፤

፰፫ እና እነርሱ ደግሞም እንደ ሰዎች በሥጋ ይፈረድባቸው ዘንድ ወልድ የጎ በኛቸው፣ እናም ᵐወንጌሉንም ᵃየሰበከላ ቸው ሐበወኅኒ ውስጥ የነበሩ የሰዎች ᵐነፍ ሳት ናቸው፤

፰፬ በስጋ የኢየሱስን ᵐምስክር ያልተቀ በሉ፣ ነገር ግን በኋላ የተቀበሉት ናቸው።

፰፭ እነዚህ በምድር የተከበሩ፣ በሰዎች ተንኮል ምክንያት የታወሩ ሰዎች ናቸው።

፰፮ እነርሱ ክብሩን ቢቀበሉም፣ ሙላቱን ግን የማይቀበሉ ናቸው።

፰፯ እነዚህ የወልድን መገኘት ቢቀበ ሉም፣ የአብን ሙላት የማይቀበሉ ናቸው።

፰፰ ስለዚህ፣ ᵐየተረስትሪያል ሰውነቶች እንጂ የሰለስቲያል ሰውነቶች አይደሉምና፣ እናም ጨረቃ ከጸሀይ ልዩ እንደሆነም ክብ ሩም እንዲሁ ልዩ ነው።

፰፱ እነዚህም በኢየሱስ ምስክርነት ᵐደፋር ያልሆኑት ናቸው፤ ስለዚህ፣ የአምላካችንን መንግስት አክሊል አይቀበሉም።

፱ እናም አሁን ይህም በመንፈስ እያለን ጌታ እንድንፅፈው ያዘዘን ስለ ተረስትሪያል ያየነው ራዕይ መጨረሻ ነው።

፱፩ እና ደግሞም፣ እንዲሁም በጠፈር ውስጥ የኮከብ ክብር ከጨረቃ ክብር ልዩ

፰፬ ᵐ ራዕ. ፭፡፲፮።
፰፭ ᵐ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
፰፮ ᵐ ቅ.መ.መ. ፅዮን።
ᵃ ኢሳ. ፭፬፡፭፫፤ ዕብ. ፲፪፡፳፪–፳፬፤ ራዕ. ፲፡፩፤ ት. እና ቃ. ፹፬፡፪፤ ፻፴፣ ፻፶።
፰፯ ᵐ ት. እና ቃ. ፻፭፡፱–፲፪።
፶፩ ሁሉንም ነገሮች ᵐይረዳል፣ እና ሁሉም ነገሮች በፊቱ ናቸው፣ እና ሁሉም ነገሮች በዙሪያው ናቸው፤ እና በሁሉም ነገሮች ላይ፣ በሁሉም ነገሮች ውስጥ ነው፣ እና በሁሉም ነገሮች ከዳር እስከ ዳር ነው፤ እና ሁሉም ነገሮች በእርሱ፣ እና በእርሱ በኩል፣ እንዲሁም በእግዚአብሔር፣ ለዘ ለአለም ናቸው።

፶፪ እና ዳግም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ለሁሉም ነገሮች ᵐበጊዜአቸው እና በወቅ ታቸው የሚሄዱበት ህግ ሰጥቷል፤

፶፫ እናም መንገዶቻቸውም፣ እንዲሁም ምድርን እና ፕላኔቶችን የሚያካትቱት የሰ ማያት እና የምድር መንገዶች፣ የተወሰኑ ናቸው።

፶፬ እናም በጊዜአቸው እና በወቅታቸ ውም፣ በደቂቃዎቻቸው፣ በሰአቶቻቸው፣ በቀናቶቻቸው፣ በሳምንቶቻቸው፣ በወራ ቶቻቸው፣ በአመቶቻቸው እርስ በራስ ᵐብርሀን ይሰጣሉ—እነዚህም ሁሉ ለእግ ዚአብሔር ᵃአንድ አመት ናቸው፣ ነገር ግን ለሰው አይደሉም።

፶፭ ምድር በክንፎቿ ትሽከረከራለች፣ እናም ᵐጸሀይ ብርሀኑን በቀን ይሰጣል፣ እና ጨረቃም ብርሀኗን በማታ ትሰጣለች፣ እና ከዋክብትም፣ በእግዚአብሔር ᵃሀይል መካ ከል በክብር በክንፎቻቸው ሲሽከረከሩ፣ ብርሀናቸውን ይሰጣሉ።

፶፮ እንዲገባችሁ፣ እነዚህን መንግስታት ከምን ጋር ላመሳስል?

፶፯ እነሆ፣ እነዚህ ሁሉ መንግስታት ናቸው፣ እናም ማንኛውን ወይም ከእነዚህ ታናሾችን ያየ ማንም ሰው እግዚአብሔር በሞገሱ እና በክብሩ ሲሄድ ᵐአይቶታል።

፶፰ እላችኋለሁ፣ እርሱ አይቶታል፤ ይህም ቢሆን፣ ᵐየራሱ ወደ ሆኑት የመጣ ውንም አልተቀበሉትም።

፶፱ ᵐብርሀንም በጭለማ ያበራል፣ እና በጨለማም ያሉት አይረዱትም፤ ይህም ቢሆን፣ በእርሱ ውስጥ እና በእርሱ ህይ ወት ተሰጥቷችሁ እግዚአብሔርን ᵃየምት ረዱበት ቀን ይመጣል።

፷ ከዚያም እንዳያችሁኝ፣ እንደሆንኩኝ፣ እና በውስጣችሁ ያለሁት የእውነት ብርሀን እንደሆንኩኝ፣ እና እናንተም በእኔ ውስጥ እንዳላችሁ ታውቃላችሁ፤ አለበለዚያም ውጤታማ አትሆኑም።

፷፩ እነሆ፣ እነዚህን መንግስታት እርሻ ባለው ሰው አመሳስላቸዋለሁ፣ እናም አገ ልጋዮቹ እርሻውን ይቆፍሩ ዘንድ ወደ እር ሻው ላካቸው።

፷፪ እና ለመጀመሪያው እንዲህ ይላል፥ ሂድ እና በእርሻው ስራ፣ እና በመጀመሪ ያው ሰዓት ወደአንተ እመጣለሁ፣ እና የፊቴ ደስታን ታያለህ።

፷፫ እና ለሁለተኛውም እንዲህ ይላል፥ አንተ ደግመህ ወደ እርሻው ሂድ፣ እና በሁ ለተኛው ሰዓት በፊቴ ደስታ እጎበኝሀለሁ።

፷፬ እና ደግሞም ለሶስተኛውም አለ፥ እጎ በኝሀለሁ።

፷፭ እና ለአራተኛውም፣ እና ቀጥሎም ለአስራ ሁለቱ።

፷፮ በመጀመሪያው ሰዓት የእርሻው ጌታ ወደ መጀመሪያው ሄደ፣ እና በዚያ ሰዓት ሁሉ ከእርሱ ጋር ቆየ፣ እና እርሱም በጌ ታው ፊት ብርሀን ተደሰተ።

፷፯ እና ከዚያም ሁለተኛውን፣ እና ሶስተ ኛውን፣ እና አራተኛውን፣ እና እስከ አስራ ሁለተኛው ድረስ ደግሞ ለመጎብኘት ከመ ጀመሪያው ተለይቶ ሄደ።

፶፩ ᵐ ፩ ዮሐ. ፫፡፳፣
፩ ኔፊ ፱፡፮፣
፪ ኔፊ ፱፡፳፣
ት. እና ቃ. ፴፰፡፩–፫።
ቅ.መ.መ. ሁሉን የሚያውቅ።
፶፪ ᵐ ዳን. ፪፡፳–፳፪፣
አብር. ፫፡፪–፲፱።
፶፫ ᵐ ቅ.መ.መ. ብርሀን፣
የክርስቶስ ብርሀን።
ᵃ መዝ. ፶፡፪፣
፪ ጴጥ. ፫፡፰።
፶፭ ᵐ ዘፍጥ. ፩፡፲፮፣
አብር. ፱፡፲፯።
ᵃ ት. እና ቃ. ፹፰፡፲–፲፫።
፶፯ ᵐ አልማ ፴፡፶፪፣
ሙሴ ፩፡፳፯–፳፰፣ ፮፡፳፫፣
አብር. ፫፡፳፩።
፶፰ ᵐ ዮሐ. ፩፡፲፩፣
፫ ኔፊ ፱፡፲፯፣
ት. እና ቃ. ፴፱፡፩–፪።
፶፱ ᵐ ት. እና ቃ. ፮፡፳፩፣
፶፡፳፫–፳፬፣ ፹፡፪፡ ፹፡፶፭–፶፯።
ᵃ ዮሐ. ፲፯፡፫፣
ት. እና ቃ. ፶፫፡፩፣ ፳፡፳፯።

፶፰ እንደዚሁ ሁሉም፣ እያንዳንዱ በሰዓቱ፣ እና በጊዜው፣ እና በወቅቱ፣ የጌታቸውን ፊት ብርሀን ተቀበሉ—

፶፱ ከመጀመሪያው ጀምሮ፣ እና ᵁእስከ መጨረሻው በመቀጠል፣ እና ከመጨረሻው እስከመጀመሪያው፣ እና ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው እንዲህ ተቀበሉ፤

፷ ጌታው በእርሱ እና እርሱም በጌታው፣ ይከብር ዘንድ፣ ሁሉም ይከብሩ ዘንድ፣ እያንዳንዱም ሰው ሰዓቱ እስኪያልቅ ድረስ፣ እንዲሁም ጌታው እንዳዘዘው እንዲሁ ተቀበለ።

፷፩ ስለዚህ፣ በዚህ ምሳሌ እነዚህን መንግስታት፣ እና ᵁየሚኖሩባቸውን፣ እንዲሁም በሰአቱ፣ እና በጊዜው፣ እና በወቅቱ፣ እንዲሁም እግዚአብሔር ባወጀው ያሉትን እያንዳንዱ መንግስት እመስላለሁ።

፷፪ እና ዳግም፣ ᵁባልንጀሮቼ፣ እውነት እላችኋለሁ፣ በቅርብ እያለሁ ᴸእንድትጠሩኝ ዘንድ፣ ከምሰጣችሁ ከዚህ ትእዛዝ ጋር፣ እነዚህን አባባሎች በልባችሁ ᴴእንድታሰላስሏቸው እተውላችኋለሁ—

፷፫ ወደ እኔ ᵁቅረቡ እና እኔም ወደ እናንተ እቀርባለሁ፤ ተግታችሁም ᴸፈልጉኝ እናም ᴴታገኙኝማላችሁ፤ ለምኑ፣ እናም ይሰጣችኋል፤ አንኳኩ፣ ይከፈትላችሁማል።

፷፬ ለእናንተ ᵁአስፈላጊ የሆነውን ማንኛውንም ነገር በስሜ አብን ᴸብትለምኑ፣ ይሰጣችኋል።

፷፭ እናም ለእናንተ ᵁአስፈላጊ ያልሆነውን ብትጠይቁ፣ ወደ ᴸኩነኔም ይቀየርባችኋል።

፷፮ እነሆ፣ የምትሰሙት በምድረበዳ እንደሚጮኽ ሰው ᵁድምፅ ነው—በምድረበዳ፣ ምክንያቱም ልታዩት አትችሉምና—ድምጼ፣ ምክንያቱም ድምጼ ᴸመንፈስ ነውና፤ መንፈሴም እውነት ነው፤ ᴴእውነትም ይጸናልና መጨረሻም የለውም፤ እና በእናንተ ቢሆንም ይበዛል።

፷፯ እና ወደ ᵁክብሬ ዐይኖቻችሁ ᴸቢያተኩሩ፣ ሰውነታችሁ ሁሉ ብሩህ ይሆናል፣ እና በእናንተም ምንም ጭለማ አይኖርም፤ እና ብሩህ የሆነ ሰውነትም ሁሉንም ነገሮች ᴴይረዳል።

፷፰ ስለዚህ፣ ᵁአዕምሮዎቻችሁ ለእግዚአብሔር የቀኑ እንዲሆኑ ራሳችሁን ᴸቀድሱ፣ እናም እርሱን ᴴየምታዩበት ቀን ይመጣል፤ ፊቱን ለእናንተ ይገልጣልና፣ እና ይህም በራሱ ጊዜና፣ በራሱ መንገድ፣ እናም እንደ ፈቃዱ ይሆናል።

፷፱ የሰጠኋችሁን ታላቅ እና የመጨረሻ ቃል ኪዳን አስታውሱ፤ ᵁከንቱ ሀሳቦቻችሁንና ከልክ በላይ የሆኑ ᴸሳቆችን ከእናንተ አስወግዱ።

፸ ቆዩ፣ በዚህም ስፍራ ቆዩ፣ እና የክብር ስብሰባን፣ እንዲሁም በእዚህ በመጨረሻው መንግስት የመጀመሪያ አገልጋዮች የሆኑትን፣ ጥሩ።

፸፩ እናም ያስጠነቀቋቸውም በጉዞአቸው ጌታን ይጥሩ፣ እና ለጥቂት ወቅትም የተ

፶፱ ሀ ማቴ. ፳፥፩–፲፮።
፷፩ ሀ ት. እና ቃ. ፸፯፥፫፬።
፷፪ ሀ ት. እና ቃ. ፹፬፥፷፫፤
፺፫፥፵፭።
ለ ኢሳ. ፶፭፥፮፤
ያዕ. ፩፥፭፤
ት. እና ቃ. ፵፮፥፯።
ሐ ቅ.መ.መ. ማሰላሰል።
፷፫ ሀ ዘካ. ፩፥፫፤
ያዕ. ፬፥፰፤
ራዕ. ፫፥፳።
ለ ፩ ዜና ፳፰፥፱፤
ኤተር ፲፪፥፵፩፤
ት. እና ቃ. ፻፩፥፴፰።
ሐ ት. እና ቃ. ፬፥፯፤ ፵፱፥፳፮።
፷፬ ሀ ት. እና ቃ. ፲፰፥፲፰፤
፵፮፥፳፰–፴።
ለ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
፷፭ ሀ ያዕ. ፬፥፫።
ለ ት. እና ቃ. ፷፫፥፯–፲፩።
፷፮ ሀ ኢሳ. ፵፥፫፤
፩ ኔፊ ፲፯፥፲፫፤
አልማ ፭፥፴፯–፴፰፤
ት. እና ቃ. ፻፳፰፥፳።
ለ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ፤
ብርሀን፣ የክርስቶስ ብርሀን።
ሐ ቅ.መ.መ. እውነት።
፷፯ ሀ ዮሐ. ፯፥፲፰።
ለ ማቴ. ፮፥፳፪፤
ሉቃ. ፲፩፥፴፬–፴፮፤
ት. እና ቃ. ፹፪፥፲፱።
ሐ ምሳ. ፳፰፥፭፤
ት. እና ቃ. ፺፫፥፳፰።
ቅ.መ.መ. የመለየት ስጦታ።
፷፰ ሀ ቅ.መ.መ. አዕምሮ።
ለ ቅ.መ.መ. ቅድስና።
ሐ ት. እና ቃ. ፷፯፥፲–፲፫፤
፺፫፥፩፤ ፺፯፥፲፭–፲፯።
፷፱ ሀ ማቴ. ፲፪፥፴፮፤
ሞዛያ ፬፥፳፱–፴፤
አልማ ፲፪፥፲፬።
ለ ት. እና ቃ. ፶፱፥፲፭፤
፹፰፥፻፳፩።

ቀበሉትን ᵐማስጠንቀቂያ በልቦቻቸው ያሰ
ላስሉ።

፫፪ እነሆ፣ እናም አስተውሉ፣ መንጋ
ዎቻችሁን እንከባከባለሁ፣ እና ሽማግሌ
ዎችን አስነሳለሁ እና ወደ እነርሱም እል
ካለሁ።

፫፫ እነሆ፣ ስራዬን በራሱ ጊዜ አፈጥና
ለሁ።

፫፬ እናም የዚህ የመጨረሻ መንግስት
የመጀመሪያ ᵐአገልጋዮች ለሆናችሁ፣
አብራችሁ እንድትሰበሰቡ፣ እና ራሳችሁን
እንድታደራጁ፣ እና ራሳችሁን እንድታዘ
ጋጁ፣ እና ራሳችሁን ᵃትቀድሱ ዘንድ ትእ
ዛዝ እሰጣችኋለሁ፤ አዎን፣ ᵇአነጻችሁም
ዘንድ ልባችሁን አንጹ፣ እጆቻችሁን እና
እግሮቻችሁንም በፊቴ ᶜየጸዱ ይሁኑ፤

፫፭ ከዚህ ክፉ ትውልድ ደም ንጹህ መሆ
ናችሁን ወደ ᵐአባታችሁ፣ አምላካችሁና፣
አምላኬ፣ እመሰክር ዘንድ፤ እንደ ፈቃዴም
የገባሁላችሁ ቃል ኪዳን፣ ይህን ታላቅ እና
የመጨረሻ ቃል ኪዳን፣ ላሟላ እችል ዘንድ
ነው።

፫፮ ደግሞም፣ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ᵐበጸ
ሎት እና ᵃበጾም ትበረቱም ዘንድ ትእዛዝ
እሰጣችኋለሁ።

፫፯ እናም የመንግስቱን ᵐትምህርት እርስ
በርስ ᵃትማማሩም ዘንድ ትእዛዝ እሰጣች
ኋለሁ።

፫፰ በትጋት አስተምሩ እናም፣ ᵐጸጋዬ
ከእናንተ ጋር ይሆናል፣ ይህም በፅንሰ
ሀሳብ፣ በመሰረታዊ መርሆች፣ በትምህ
ርት፣ በወንጌሉ ህግ፣ ከእግዚአብሔር መን
ግስት ጋር ግኑኝነት ባላቸው ሁሉም ነገሮች፣
ለእውቀታችሁ አስፈላጊ የሆኑትን ፈጽማ
ችሁ ᵃእንድትማሩ ዘንድ፤

፫፱ ᵐበሰማይና ምድር፣ እናም ከምድር
በታች፣ ስላሉትም ነገሮች፤ ስለነበሩት ነገ
ሮች፣ ስለአሉ ነገሮች፣ እና በቅርብም ስለ
ሚሆኑት ነገሮች፤ በቤት ስላሉም ነገሮች፣
በሌሎች ሀገሮች ስላሉትም ነገሮች፤ ስለህ
ዝብ ᵃጦርነቶች እና አወዛጋቢ ጉዳዮች፣ እና
በምድር ላይ ስላሉት ፍርዶች፤ እና የሀገ
ራት እና የመንግስታትም እውቀቶች በፍ
ጹም እንድትማሩ ዘንድ፣ ጸጋዬ ከእናንተ
ጋር ይሆናል—

፴ በተጠራችሁበት ጥሪ፣ እና በልዩ ሀላ
ፊነት በሰጠኋችሁ ተልዕኮ፣ ጥሪዎቻች
ሁን እንድታጎሉ በምልካችሁ ጊዜ በሁ
ሉም ነገሮች ትዘጋጁ ዘንድ ጸጋዬ ከእና
ንተ ጋር ይሆናል።

፴፩ እነሆ፣ የላኳችሁ ᵐእንድትመሰክሩ
እና ሰዎችን ᵃእንድታስጠነቅቁ ነው፣ እናም
የተጠነቀቀው ሰው ባልንጀራውን ማስጠን
ቀቁ አስፈላጊ ነው።

፴፪ ስለዚህ፣ ምክንያትም አይኖራቸ
ውም፣ እና ኃጢአቶቻቸውም በራሳቸው
ላይ ናቸው።

፴፫ ከጊዜው ᵐቀድሞ ᵃየሚፈልገኝም ያገ
ኘኛል፣ እና አይተውም።

፴፬ ስለዚህ ለመጨረሻ ጊዜ ᵐበአህዛብ
መካከል በመሄድ በአገልግሎታችሁ ፍጹ
ማን ትሆኑ ዘንድ፤ የጌታም አንደበት የጠ
ራቸውን ሁሉ ለማምጣት፤ ህግን ᵃለማሰር
እና ምስክርንም ለማተም እና ከሚመጣ
ውም የፍርድ ሰአት ቅዱሳንን ታዘጋጁ ዘንድ
ቆዩ እናም ተግታችሁም ስሩ።

፫፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. ማስጠንቀቅ፣
ማስጠንቀቂያ።
፫፩ *ሀ* ማቴ. ፳፡፩፤ ፲፯።
ለ ዘሌዋ. ፳፡፲፯–፳፡
፫ ኔፊ ፲፱፡፳፰–፳፱፤
ት. እና ቃ. ፱፡፳፰–፳፱፤
፻፴፫፡፳፪።
ሐ ቅ.መ.መ. ንጹህ እና ርኩስ።
መ ኤተር ፲፪፡፴፯።
፫፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. ሰው፣ ሰዎች—
ሰው፣ የሰማይ አባት
የመንፈስ ልጅ፤
እግዚአብሔር፣ አምላክ—
እግዚአብሔር አብ፤
የሰማይ አባት።
፫፪ *ሀ* ቅ.መ.መ. ጸሎት።
ለ ቅ.መ.መ. ጾም፣ መጾም።
፫፪ *ሀ* ቅ.መ.መ. የክርስቶስ
ትምህርት።
ለ ቅ.መ.መ. ማስተማር፣
አስተማሪ።
፫፫ *ሀ* ቅ.መ.መ. ጸጋ።
ለ ት. እና ቃ. ፲፡፳፡፲፳፤
፻፡፲፭፤ ፻፲፡፻፲።
፫፬ *ሀ* ቅ.መ.መ. ሰማይ።
ለ ቅ.መ.መ. ጦርነት።
፲፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. መመስከር።
ለ ት. እና ቃ. ፳፡፲፡፻፳።
ቅ.መ.መ. ማስጠንቀቅ፣
ማስጠንቀቂያ።
፲፩ *ሀ* አልማ ፴፯፡፴፤ ፴፭።
ለ ዘዳግ. ፬፡፳፱–፴፩፤
ኤር. ፳፱፡፲፱–፲፰፤
ት. እና ቃ. ፶፬፡፲።
፲፩ *ሀ* ጆ.ስ.—ታ. ፭፡፴፭።
ለ ኢሳ. ፳፡፲፯–፲፯።

፹፭ ነፍሳቸውም በዚህም ሆነ በሚመጣው አለም ክፉዎችን የሚጠብቀውን፣ [ሀ]የርኩሰጥ ጥፋት የሆነውን፣ የእግዚአብሔር ቁጣ ያመልጥ ዘንድ ቅዱሳንን ታዘጋጁ ዘንድ ቆዩ እናም ተግታችሁም ስሩ። እውነት እላችኋለሁ የጌታ አንደበት [ለ]እስኪጠራቸው ድረስ የመጀመሪያ ያልሆኑት ሽማግሌዎች በወይኑ ስፍራ መስራታቸውን ይቀጥሉ፤ ሰአታቸው ገና አልደረሰምና፤ ልብሶቻቸውም ከዚህ ትውልድ ደም [ሐ]የነጹ አይደሉም።

፹፮ [ሀ]ነጻ ሆናችሁ በተፈጠራችሁበትም [ለ]አርነት ጸንታችሁ ቁሙ፤ [ሐ]በኃጢአትም ራሳችሁን [መ]አትጥመዱ፣ ነገር ግን፣ ጌታ እስከሚመጣ ድረስ፣ እጆቻችሁን [ሠ]እንዲጸዱ አድርጉ።

፹፯ ለብዙ ቀናት ሳይቆይ እና [ሀ]ምድርም እንደሰካራም ሰው [ለ]ትፍገመገማለች እና ወዲህና ወዲያ ትናወጣለች፣ እና [ሐ]ጸሀይም ፊቷን ትሰውራለች፣ ብርሀኗንም ትከለክላለች፤ እና ጨረቃም [መ]በደም ትርሳለች፤ እና [ሠ]ከዋክብትም እጅግ ይቆጣሉ፣ እናም የበለስ ፍሬ ከበለስ እንደሚወድቅም ራሳቸውን ይጥላሉ።

፹፰ እና ከምስክርነታችሁ በኋላ በህዝብ ላይ ንዴት እና ቁጣ ይመጣል።

፹፱ ከምስክርነታችሁ በኋላ፣ በመካከሏ ሁከት የሚያመጣ የምድር [ሀ]መናወጥ ምስክርነት ይመጣል፣ እና ሰዎችም ወደ ምድር ይወድቃሉ እናም ለመነሳትም ይሳናቸዋል።

፺ እና ደግሞም የነጎድጓድ፣ እና የመብረቅ [ሀ]ድምፅ፣ እና የማእበል ድምፅ፣ እና ከገደባቸው በላይ ራሳቸውን በሚወረውሩ የባህር ማዕበል ድምፅ ምስክርነት ይመጣል።

፺፩ እና ሁሉም ነገሮች [ሀ]በሁከት ውስጥ ይሆናሉ፣ እና በእርግጥም፣ የሰዎች ልብ በፍርሀት ይደክማል፤ ፍርሀት በሁሉም ሰዎች ላይ ይመጣልና።

፺፪ እናም፣ ተዘጋጁ፣ ተዘጋጁ፣ በምድር የምትኖሩ ሆይ፤ የእግዚአብሔር ፍርድ መጥቷልና። እነሆ፣ እና አስተውሉ፣ [ሀ]ሙሽራው መጥቷል፤ ከእርሱ ጋር ለመገናኘትም ውጡ በማለት፣ በከፍተኛ ድምፅ በመጮህ፣ የእግዚአብሔርን መለከት በመንፋት፣ [ለ]መላዕክትም በሰማይ መካከል ይበራሉ።

፺፫ እና ወዲያውም በሰማይ [ሀ]ታላቅ ምልክት ይታያል፣ እናም ሁሉም ሰዎች አብረው ያዩታል።

፺፬ እና ሌላም መልአክ መለከቱን እንዲህ በማለት ይነፋል፥ ህዝብን ሁሉ [ሀ]የዝሙቷን ቁጣ ወይን ጠጅ እንዲጠጡ ያደረገችው፣ የእግዚአብሔን ቅዱሳን የምታሳድድ፣ ደማቸውን የምታፈስ—በብዙ ውሀዎች እና በባህር ደሴቶች ላይ የተቀመጠችው—ያቺ [ለ]ታላቅ [ሐ]ቤተክርስቲያን፣ የርኩሰት [መ]እናት፣ እነሆ፣ የምድር [ሠ]እንክርዳድ እርሷ ነች፤ አንድ ላይ ታስራለች፤ እስሯም ተጠናክሯል፣ እና ማንም ሰው ሊፈታው አይችልም፤ ስለዚህ፣ [ረ]ለመንደድ ተዘጋ

፹፭ ሀ ማቴ. ፳፬፥፲፭።
ለ ት. እና ቃ. ፲፩፥፲፭።
ሐ ፩ ኔፊ ፲፪፥፲–፲፩፤
ያዕቆ. ፩፥፲፱፤ ፪፥፪፤
ት. እና ቃ. ፻፲፪፥፴፫።
ቅ.መ.መ. ንጹህ፣ ንጹህነት።
፹፮ ሀ ሞዛያ ፭፥፰።
ቅ.መ.መ. መብት።
ለ ዮሐ. ፰፥፴፮።
ቅ.መ.መ. ነጻ ምርጫ፤
ነጻ፣ ነጻነት።
ሐ ቅ.መ.መ. ኃጢያት።
መ ገላ. ፭፥፩።
ሠ ኢዮብ ፲፯፥፱፤ መዝ. ፳፬፥፬፤
አልማ ፭፥፲፱።
፹፯ ሀ ኢሳ. ፲፫፥፬–፲፫።
ለ ት. እና ቃ. ፵፫፥፲፰።
ሐ ኢዩ. ፪፥፲፤
ት. እና ቃ. ፵፭፥፵፪፤
፻፴፫፥፵፱።
መ ራዕ. ፮፥፲፪።
ሠ ኢዩ. ፫፥፲፭።
፹፱ ሀ ት. እና ቃ. ፵፭፥፴፫።
፺ ሀ ራዕ. ፰፥፭፤
ት. እና ቃ. ፵፫፥፲፯–፳፭።
፺፩ ሀ ት. እና ቃ. ፵፭፥፳፮።
፺፪ ሀ ማቴ. ፳፭፥፩–፲፫፤
ት. እና ቃ. ፴፫፥፲፯፤
፻፴፫፥፲፣ ፲፱።
ለ ራዕ. ፰፥፲፫፤
ት. እና ቃ. ፻፴፫፥፲፯።
፺፫ ሀ ማቴ. ፳፬፥፴፤
ሉቃ. ፳፩፥፳፭–፳፯።
ቅ.መ.መ. የጊዜዎች
ምልክቶች።
፺፬ ሀ ራዕ. ፲፬፥፰።
ለ ፩ ኔፊ ፲፫፥፬–፱።
ሐ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ—
የዲያብሎስ ቤተክርስቲያን።
መ ራዕ. ፲፯፥፭።
ሠ ማቴ. ፲፫፥፴፰።
ረ ት. እና ቃ. ፳፬፥፳፫–፳፬፤
፻፩፥፳፫–፳፭።
ቅ.መ.መ. ምድር—
ምድርን ማፅዳት።

ጅታለች። እና መለከቱም ረጅም እና ጉልህ ይሆናል፤ እና ሁሉም ህዝብ ይሰሙታል።

፺፭ እና በሰማይም ለግማሽ ሰአት ያህል [ሀ]ጸጥታ ይሆናል፤ እና ወዲያውም፣ መጽሐፍ [ለ]ጥቅልል ከተጠቀለለ በኋላ እንደሚዘረጋ፣ የሰማይ መጋረጃዎች ይዘረጋሉ፣ እናም የጌታ [ሐ]ፊትም ይገለጣል፤

፺፮ እና በህይወት በምድር ላይ ያሉት ቅዱሳን በቅፅበት ይለወጣሉ እና እርሱን ያገኙት ዘንድም [ሀ]ይነጠቃሉ።

፺፯ እና በየመቃብራቸው ያንቀላፉትም [ሀ]ይነሳሉ፣ መቃብሮቻቸውም ይከፈታሉና፤ እና እነርሱ ደግመውም በሰማይ አምድ መካከል እርሱን ለመቀበል ይነጠቃሉ—

፺፰ መጀመሪያ ከእርሱ ጋር የሚወርዱት፣ እና በምድርና በመቃብራቸው ያሉት፣ እርሱን ለመቀበል የተነጠቁት፣ እነርሱም የክርስቶስ፣ [ሀ]የመጀመሪያ ፍሬዎች፣ ናቸው፤ እና ይህም ሁሉ የሚሆነው የእግዚአብሔር መልአክ መለከት ድምፅ ሲሰማ ነው።

፺፱ ከዚህ በኋላም ሌላ መልአክ፣ ሁለተኛው መለከት፣ ያሰማል፤ ከዚያም፣ ወንጌልን ለመቀበልና እንደሰዎች በሥጋ [ሀ]ይፈረድባቸው ዘንድ፣ [ለ]በወህኒ ለእነርሱ የተዘጋጀውን ድርሻቸውን የተቀበሉት፣ በመምጫው ጊዜ የክርስቶስ የሆኑት ቤዛነትም ይመጣል።

፻ ደግሞም፣ ሶስተኛው መለከት የሆነው ሌላ መለከት ይነፋል፤ ከዚያም የሚፈረድባቸውና [ሀ]በኩነኔ የሚገኙት ሰዎች [ለ]ነፍሳት ይመጣሉ፤

፻፩ እነዚህም የቀሩት [ሀ]ሙታን ናቸው፤ እና ይህ [ለ]ሺህ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ፣ ያም እስከምድር ፍጻሜም ድረስ፣ በሕይወት አይኖሩም።

፻፪ እና አራተኛው መለከት የሆነው ሌላ መለከትም እንዲህ በማለት ይነፋል፥ እስ ከታላቅ እና መጨረሻው ዘመን፣ እንዲሁም እስከፍጻሜው፣ ድረስ ከሚቀሩት መካከል [ሀ]ቆሸሸው የሚቀሩ አሉ።

፻፫ እና አምስተኛው መለከት የሆነው፣ [ሀ]ዘለአለማዊውን ወንጌል በሰማይ መካከል በመብረር ለሀገር ለነገድ ለቋንቋ ለህዝብ የሚሰብከው አምስተኛው መልአክ፣ ሌላውን መለከት ይነፋል፤

፻፬ ይህም፣ ለህዝብ ሁሉ በማለት፣ የመለከቱ ድምፅ ይሆናል፣ በሰማይና በምድር፣ እና ከምድር በታች ላሉት—[ሀ]ሁሉም ጆሮዎች ይሰሙታልና፣ እና የመለከቱንም ድምፅ እንዲህ ሲል ሲሰሙም፣ ጉልበት ሁሉ [ለ]ይንበረከካል ምላስም ሁሉ ይናዘዛል፥ እግዚአብሔርን [ሐ]ፍሩ፣ እና በዙፋኑ ላይ ከዘለአለም እስከ ዘለአለም ለሚቀመጠው ክብሩን ስጡ፤ የፍርዱ ሰዓት ደርሶአልና።

፻፭ እና ደግሞም፣ ስድስተኛው መልአክ የሆነው ሌላ መልአክም መለከቱን እንዲህ በማለት ይነፋል፥ ህዝብን ሁሉ የዝሙቷን ቁጣ ወይን ጠጅ እንዲጠጡ ያደረገችው [ሀ]ወድቃለች፤ ወድቃለች፣ ወድቃለች!

፻፮ እና ዳግም፣ ሰባተኛው መልአክ የሆነው ሌላ መልአክ መለከቱን እንዲህ በማለት ይነፋል፥ ተፈፅሟል፤ ተፈፅሟል! የእግዚአብሔር [ሀ]በግ [ለ]አሸንፎታል እናም መጥመቂያውን፣ እንዲሁም ሁሉን የሚገዛ የእግዚ

፺፭ ሀ ት. እና ቃ. ፴፰፥፲፪።
ለ ራዕ. ፮፥፲፬።
ሐ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
፺፮ ሀ ፩ ተሰ. ፬፥፲፮–፲፯።
፺፯ ሀ ት. እና ቃ. ፳፱፥፲፫፤ ፵፭፥፵፭–፵፮፤ ፻፴፫፥፶፮። ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
፺፰ ሀ ፩ ቆሮ. ፲፭፥፳፫።
፺፱ ሀ ፩ ጴጥ. ፬፥፮።
ለ ት. እና ቃ. ፸፮፥፸፫፤ ፻፴፰፥፴። ቅ.መ.መ. ለሙታን ደህንነት።
፻ ሀ ቅ.መ.መ. መኮነን፣ ኩነኔ።
ለ ራዕ. ፳፥፲፪–፲፫፤ አልማ ፲፩፥፵፩፤ ት. እና ቃ. ፸፮፥፲፯፤ ፸፮፥፹፭።
፻፩ ሀ ራዕ. ፳፥፭።
ለ ቅ.መ.መ. አንድ ሺህ አመት።
፻፪ ሀ ቅ.መ.መ. እድፍ፣ እድፍነት።
፻፫ ሀ ራዕ. ፲፬፥፮–፯። ቅ.መ.መ. የወንጌል ዳግም መመለስ።
፻፬ ሀ ራዕ. ፭፥፲፫።
ለ ኢሳ. ፵፭፥፳፫፤ ፊልጵ. ፪፥፱–፲፩።
ሐ ቅ.መ.መ. ማክበር፤ ፍርሀት—እግዚአብሔርን መፍራት።
፻፭ ሀ ራዕ. ፲፬፥፰፤ ት. እና ቃ. ፩፥፲፮።
፻፮ ሀ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር በግ።
ለ ፩ ቆሮ. ፲፭፥፳፭።

አብሔርን የብርቱ ቍጣውን ወይን መጥመቂያን፣ ብቻውን ᵃረግጦታል።

፲፯ ከዚያም መላእክቱ የሀይሉን የክብር አክሊል ይደፋሉ፣ እና ᵇቅዱሳንም ᵃበክብሩ ይሞላሉ፣ እና ᶜውርሳቸውን ይቀበላሉ እና ከእርሱም ጋር ᵐእኩል ይደረጋሉ።

፲፰ ከዚያም የመጀመሪያው መልአክ መለከቱን ዳግም በሚኖሩት ጆሮዎች ላይ ያሰማል፣ እና የሰዎችን የሚስጥር ስራዎችና ᵇበመጀመሪያው ሺህ አመታት የእግዚአብሔርን ታላቅ ስራዎች ᵃይገልጣል።

፲፱ ከዚያም ሁለተኛው መልአክ መለከቱን ይነፋል፣ እና የሰዎችን የሚስጥር ስራዎች፣ እና የልባቸውን ሀሳብና ስሜታቸውን፣ እና በሁለተኛው ሺህ አመታት የእግዚአብሔርን ታላቅ ስራዎች ይገልጣል—

፲፡ እናም ሰባተኛው መልአክ መለከቱን እስከሚነፋ ድረስ ይቀጥላል፤ እና በምድር ላይ እና በባህር ላይ ይቆማል፣ እና ᵇዘመንም እንደሚፈጸም በዙፋኑ ላይ በሚቀመጠው ስም ይምላል፤ እና የቀደመውንም እባብ፣ ዲያብሎስ የሚባለው፣ ᵃሰይጣንም ይያዛል፣ እና ᶜለአንድ ሺህ ለሚሆን ዘመንም አይፈታም።

፲፡፩ ከዚያም ሰራዊቱን ለመሰብሰብ ይችል ዘንድ ለትንሽ ዘመን ᵇይለቀቃል።

፲፡፪ እና ሰባተኛው መልአክ ᵇሚካኤል፣ እንዲሁም የመላእክት አለቃው፣ ሰራዊቱን፣ እንዲሁም የሰማይ ሰራዊትን፣ ይሰበስባል።

፲፡፫ እና ዲያብሎስም ሰራዊቱን ይሰበስባል፤ እንዲሁም የሲኦል ሰራዊትን፣ እና ከሚካኤልና ከሰራዊቱ ጋር ለመዋጋት ይመጣል።

፲፡፬ ከዚያም የታላቁ እግዚአብሔር ᵇጦርነት ይመጣል፤ እና በቅዱሳን ላይ ከዚህ በኋላ ሀይል እንዳይኖራቸው፣ ዲያብሎስና ሰራዊቱ ወደራሳቸው ስፍራም ይጣላሉ።

፲፡፭ ሚካኤል ጦርነታቸውን ይዋጋላቸዋልና፣ እና በዙፋኑ ላይ የተቀመጠውን፣ እንዲሁም የበጉን፣ ዙፋን ᵇየሚፈልገውን ያሸንፋል።

፲፡፮ ይህም የእግዚአብሔርና ᵇየተቀደሱት ክብር ነው፤ እና ከዚህም በኋላ ᵃሞትን አይቀምሱም።

፲፡፯ ስለዚህ፣ ᵇባልንጀሮቼ፣ እውነት እላችኋለሁ፣ እንዳዘዝኳችሁ የክብር ስብሰባችሁን ጥሩ።

፲፡፰ እና ሁሉም እምነት ስለሌላቸው፣ ተግታችሁ ፈልጉ እና እርስ በርሳችሁም ᵇየጥበብ ቃላትን ᵃተማማሩ፤ አዎን፣ ከተመረጡት ᶜመጽሀፍትም የጥበብን ቃላት ፈልጉ፤ እውቀትን፣ እንዲሁም በጥናትና ደግሞም በእምነት፣ እሹ።

፲፡፱ ራሳችሁን አደራጁ፤ አስፈላጊ ነገሮችን ሁሉ አዘጋጁ፤ ᵇቤትን፣ እንዲሁም የጸሎትን ቤት፣ የጾምን ቤት፣ የእምነትን ቤት፣ የእውቀትን ቤት፣ የክብርን ቤት፣ የስርዓትን ቤት፣ የእግዚአብሔርን ቤት መስርቱ፤

፲፯ሐ ኢሳ. ፳፫፡፫–፬፤
ራዕ. ፲፱፡፲፯፤
ት. እና ቃ. ፫፯፡፲፯፤
፲፴፫፡፱።
፲፯ ለ ቅ.መ.መ. ቅዱሳን።
ለ ቅ.መ.መ. የስለስቲያል ክብር።
ሐ ቅ.መ.መ. ከፍተኛነት።
መ ት. እና ቃ. ፫፯፡፲፯–፲፰።
፲፰ ለ ት. እና ቃ. ፫፯፡፲–፲።
ለ አልማ ፴፯፡፲፰፤
ት. እና ቃ. ፩፡፫።
፲፡ ለ ት. እና ቃ. ፹፡፱፡፱።
ለ ራዕ. ፳፡፩–፫፤
፩ ኔፊ ፳፪፡፳፯፤
ት. እና ቃ. ፲፩፡፳፰።
ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
ሐ ቅ.መ.መ. አንድ ሺህ አመት።
፲፡፩ ለ ት. እና ቃ. ፳፱፡፳፪፤
፯፫፡፴–፴፩።
፲፡፪ ለ ቅ.መ.መ. ሚካኤል።
፲፡፲ ለ ራዕ. ፲፯፡፲–፲፡
፲፡፫ ለ ኢሳ. ፲፡፲–፲፪፤
ሙሴ ፱፡፩–፱።
፲፡፭ ለ ቅ.መ.መ. ቅድስና፣
ከፍተኛነት።
ለ ራዕ. ፳፩፡፱፤
አልማ ፲፩፡፴፭፤ ፲፪፡፲፰፤
ት. እና ቃ. ፳፫፡፴፱።
ቅ.መ.መ. የማይሞት፣
አለሟችነት።
፲፡፮ ለ ት. እና ቃ. ፲፱፡፮።
፲፡፰ ለ ቅ.መ.መ. ጥበብ።
ለ ት. እና ቃ. ፹፡፲፡፡–፹።
ቅ.መ.መ. ማስተማር፣
አስተማሪ።
ሐ ት. እና ቃ. ፶፩፡፩፤
፲፱፡፲፤ ፲፡፩።
፲፡፱ ለ ት. እና ቃ. ፶፩፡፫፤
፶፯፡፲–፲፯፤ ፲፱፡፪–፱፤
፲፡፩፡፳።
ቅ.መ.መ. ቤተመቅደስ፣
የጌታ ቤት።

፲፭ በእዚህም መግባታችሁ በጌታ ስም ይሆን ዘንድ፤ መውጣታችሁም በጌታ ስም ይሆን ዘንድ፤ ሰላምታችሁም፣ ወደ ልዑል እግዚአብሔር እጆቻችሁን በማን ሳት፣ በጌታ ስም ይሆን ዘንድ የእግዚአብ ሔርን ቤት መስርቱ።

፲፭፲፩ ስለዚህ፣ ጥቅም የሌለውን ንግግራ ችሁን ሁሉ፣ [ሀ]ሳቆችን ሁሉ፣ [ለ]ከፍተኛ ፍላ ጎታችሁን ሁሉ፣ [ሐ]ኩራታችሁን እና ተራ አስተሳሰባችሁን ሁሉ፣ እና ክፉ ድርጊታ ችሁን ሁሉ [መ]አቁሙ።

፲፭፲፪ ከመካከላችሁም መምህር መድቡ፣ እና ሁሉም ታናጋሪ እንዲሆኑ አታድርጉ፤ ነገር ግን፣ ሁሉም ሲናገሩ ሁሉም ይታነጹ ዘንድ፣ እና እያንዳንዱም ሰው እኩል ባለ መብት ይሆን ዘንድ፣ አንድ በአንድ በተራ እንዲናገር አድርጉ እና ሁሉም የሚነገረ ውን እንዲሰሙ አድርጉ።

፲፭፲፫ እርስ በርሳችሁ [ሀ]መዋደዳችሁን አረ ጋግጡ፤ [ለ]ትምክህተኞች አትሁኑ፤ በወን ጌሉ አስፈላጊ እንደሆነም እርስ በርስ መካ ፈልን ተማሩ።

፲፭፲፬ [ሀ]ስራ ፈት መሆንን አቁሙ፤ እር ኩስ መሆንንም አቁሙ፤ እርስ በራስ [ለ]ስህ ተት መፈለግን አቁሙ፤ አስፈላጊ ከሆ ነው በላይ መተኛትንም አቁሙ፤ እንዳ ትደክሙ፣ ወደመኝታችሁ በጊዜ ሂዱ፤ ሰውነቶቻችሁ እና አዕምሮዎቻችሁ ይነ ቃቁ ዘንድም በማለዳ ተነሱ።

፲፭፲፭ እና ከሁሉም በላይ፣ የፍጹምነትና [ሀ]የሰላም ማሰሪያ የሆነውን [ለ]ልግስና፣ እንደ ካባ፣ ልበሱት።

፲፭፲፮ [ሀ]እስከምመጣም ድረስ ሳትታክቱ ዘንድ፣ ዘወትር [ለ]ጸልዩ። እነሆ እናም አስ ተውሉ፣ በቶሎ እመጣለሁ፣ እናም እናን ተንም ወደራሴ እወስዳችኋለሁ። አሜን።

፲፭፲፯ ደግሞም፣ ለነብያቱ [ሀ]ትምህርት ቤት አመራር፣ እንዲሁም ለቤተክርስ ቲያን [ለ]ሹማምንቶች ሁሉ፣ ወይም በሌላ ቃል፣ ከሊቀ ካህናት ጀምሮ እስከ ዲያቆን ድረስ በቤተክርስቲያኑ እንዲያገለግሉ ለተ ጠሩት ተዘጋጅቶ፣ አስፈላጊ የሆኑትን ነገ ሮች ሁሉ እንዲማሩበት የተመሰረተውን ቤት ስርዓት በሚመለከት—

፲፭፲፰ እናም ይህም የትምህርት ቤቱ አመራር ቤት ስርዓት ይሆናል፥ ፕሬዘደ ንት ወይም መምህር እንዲሆን የተሾመው በሚዘጋጅለት ቤት ውስጥ በስፍራው ቆሞ ይገኝ።

፲፭፲፱ ስለዚህ፣ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ በጎላ ንግግር ሳይሆን፣ በቤቱ ውስጥ ያሉት ተሰብሳቢዎች ቃላቶቹን በጥንቃቄና በግ ልፅ በሚሰሙበት ስፍራ መጀመሪያ ይሁን።

፲፭፳ እና ወደ እግዚአብሔር ቤት ውስጥ ሲመጣም፣ በቤቱ ውስጥ የመጀመሪያ መሆን ይገባዋልና—እነሆ፣ ይህም ድንቅ ነው፣ ምሳሌም ይሆን ዘንድ—

፲፭፳፩ የዘለአለማዊ ቃል ኪዳን ምልክት ወይም ማስታወሻም ይሆን ዘንድ፣ በጸሎት በእግዚአብሔር ፊት በመንበርከክ እራሱን [ሀ]ያቅርብ።

፲፭፳፪ እናም ከእርሱ በኋላ ማንም ሲገባ፣ መምህሩ ይነሳ፣ እና ወደሰማይ በተዘረጉ እጆች፣ አዎን፣ እንዲሁም በቀጥታ፣ ወን ድሙን ወይም ወንድሞችን በእነዚህ ቃላት ሰላም ይበላቸው፥

፲፭፳፫ እናንት ወንድም ወይም ወንድሞች ናችሁ? በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፣ በምልክት ወይም በዘለአለማዊ ቃል ኪዳን ማስታወሻ ሰላም እላችኋለሁ፣ በዚህም ቃል ኪዳን፣ በማይለወጥ፣ በማይነቃነቅ፣ እና በማይቀየር ቁርጥ ውሳኔ፣ በእግዚአብሔር

፲፭፲፩ ሀ ት. እና ቃ. ፶፱፡፲፭፣ ፲፫፡፳፱።
ለ ቅ.መ.መ. ስጋዊ።
ሐ ቅ.መ.መ. ኩራት።
መ ት. እና ቃ. ፶፫፡፴፤ ፲፡፲፯።
፲፭፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. ፍቅር።
ለ ቅ.መ.መ. መመኘት።

፲፭፲፬ ሀ ቅ.መ.መ. ስራ ሰልቺ፣ ስራ ፈቺ።
ለ ት. እና ቃ. ፴፬፡፲–፲፡ ቅ.መ.መ. ክፉ መናገር።
፲፭፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. ሰላም።
ለ ቅ.መ.መ. ልግስና።
፲፭፲፮ ሀ ት. እና ቃ. ፭፡፲፪።
ለ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
፲፭፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. የነቢያት ትምህርት ቤት።
ለ ቅ.መ.መ. ሀላፊነት፣ ሀላፊ።
፲፭፲፰ ሀ ቅ.መ.መ. ማምለክ።

ጸጋ በፍቅር እስር ውስጥ፣ በእግዚአብሔር ትእዛዛት ሁሉ ያለእንከን፣ በምስጋና መስ ጠት፣ ከዘለአለም እስከዘለአለም ጓደኛች ሁና ᵐወንድማችሁ ለመሆን ወደ ᵃማህበር ተኛነት እቀበላችኋለሁ። አሜን።

፤፲፭ እናም ለዚህ ሰላምታ ብቁ ሆኖ የማ ይገኘውም ከመካከላችሁ ምንም ስፍራ አይ ኑረው፤ ቤቴ በእርሱ ᵐእንዲረከስ አትፈቅ ዱምና።

፤፲፮ እና የሚገባውና በፊቴ ታማኝ የሚ ሆነው፣ እና ወንድም የሆነው፣ ወይም ወንድሞችም ከሆኑ፣ ወደሰማይ በተዘረጉ እጆች፣ በአንድ አይነት ጸሎት እና ቃል ኪዳን፣ ወይም በአንድ አይነት ምልክት አሜን በማለት ለፕሬዘደንት ወይም ለመ ምህሩ ሰላምታ ይሰጣሉ።

፤፲፯ እነሆ፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ይህም በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ፣ በነቢያትም ትምህርት ቤት ውስጥ፣ እርስ በርስ ሰላምታ የምትሰጣጡበት ምሳሌ ነው።

፤፲፰ እናም መሸሸጊያ፣ ለምትታነጹበት የመንፈስ ቅዱስ ᵐድንኳን ይሆን ዘንድ፣ በጌታ ቤት፣ እንዲሁም በነቢያት ትምህርት ቤት ውስጥ፣ መንፈስ በሚናገረው በምታ ደርጉት ሁሉ ጸሎት እና ምስጋና በመስጠት እንድታደርጉ ተጠርታችኋል።

፤፲፱ እና ከዚህ ትውልድ ᵐደም ንጹህ ያልሆነን በመካከላችሁ ማንንም ወደ እዚህ ትምህርት ቤት አትቀበሉ።

፤፳፩ እና እርሱም እግርን ᵐማጠብ በሆነ ስርዓት ተቀበሉት፣ ለዚህም ምክንያት ነበር የእግር ማጠብ ስነስርዓት የተመሰረተው።

፤፳፪ ደግሞም፣ የእግር ማጠብ ስርዓት የሚከናወነው በፕሬዘደንቱ፣ ወይም በቤ ተክርስቲያኗ ሽማግሌዎች አመራር ነው።

፤፳፫ ይህም የሚጀምረው በጸሎት ነው፤ እና ዳቦው እና ወይኑ ᵐከተሰጠ በኋላ፣ እኔን በሚመለከት በዮሐንስ ምስክር ምዕራፍ አስራ ሶስት ውስጥ በምስክርነት በሰጠው ᵃምሳሌ ራሱን ያልብስ። አሜን።

ክፍል ፲፱

በየካቲት ፳፯፣ ፲፰፻፳፫ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ ኦሀዮ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። በስብሰባዎቻቸው ጊዜ የቀድሞዎቹ ቅዱሳን ትምባሆ በመጠቀ ማቸው ምክንያት፣ ነቢዩ ስለጉዳዩ ያሰላሰል ዘንድ ተመርቶ ነበር፤ በዚህም ምክ ንያት፣ ስለጉዳዩ ጌታን ጠየቀ። የጥበብ ቃል ተብሎ የሚታወቀው ይህም ራዕይ የዚህ ውጤት ነበር።

፩–፱፣ የወይን ጠጅ፣ የሚያሰክሩ መጠ ጦች፣ ትምባሆ፣ እና ትኩስ መጠጦችን መጠቀም ተከልክለዋል፤ ፲–፲፯፣ የመድ ሀኒት ቅጠላቅጠል፣ ፍራፍሬዎች፣ ስጋ፣ እና እህል ለሰዎች እና ለእንስሳት ጥቅም የተመደቡ ናቸው፤ ፲፰–፳፩፣ ለወንጌሉ ህግ፣ የጥበብ ቃልን በተጨማሪ፣ ታዛዥ መሆን ስጋዊ እና መንፈሳዊ በረከቶችን ያመጣል።

፩ ᵐየጥበብ ቃል፣ በከርትላንድ ውስጥ ለተሰበሰቡት ለሊቀ ካህናት ቡድን፣ እና ለቤተክርስቲያኗ፣ እና ደግሞም ለፅዮን ቅዱሳን ጥቅም—

፤፲፫ ᵐ ቅ.መ.መ. እህት፣ ወንድሞች፣ ወንድም።
ᵃ ቅ.መ.መ. ጓደኝነት።
፤፲፬ ᵐ ት. እና ቃ. ፣፲፯፡፲፩–፲፯፣ ፤፲፯፣ ፤፲፡፣ ፯–፳።
፤፲፯ ᵐ ት. እና ቃ. ፣ ፡ ፳፡፲፩–፳፪።
፤፲፰ ᵐ ት. እና ቃ. ፲፰፡፳፡፲–፲፩።
ᵃ ቅ.መ.መ. ግንኙነት።
፤፲፱ ᵐ ቅ.መ.መ. ማጠብ፣ የታጠበ፣ የሚታጠቡ።
፤፳፩ ᵐ ቅ.መ.መ. ቅዱስ ቁርባን።
ᵃ ዮሐ. ፲፫፡፬–፲፯።
፤፲፱ ፩ ᵐ ቅ.መ.መ. የጥበብ ቃል።

፪ በትእዛዝ ወይም በማስገደድ ሳይሆን፣ ነገር ግን በራዕይ እና በጥበብ ቃል፣ በመጨረሻዎቹ ቀናት ለቅዱሳን ሁሉ በጊዜያዊ ደህንነት ውስጥ የእግዚአብሔርን ስርዓት እና [ሀ]ፈቃድ በማሳየት እንደ ሰላምታ የሚላክ፤

፫ [ሀ]ከተስፋ ጋር የሆነ መሰረታዊ መርህ፣ ለደካማው እና ቅዱሳን ለሆኑት ወይም ቅዱሳን ተብለው ለተጠሩት ደካማ [ለ]ቅዱሳን ሁሉ ችሎታ ይሆን ዘንድ የተሰጠ የጥበብ ቃል ነው።

፬ እነሆ፣ ጌታ ለእናንተ እንዲህ ይላችኋል፥ በመጨረሻዎቹ ቀናት ውስጥ [ሀ]በሚያድሙ ሰዎች ልብ ውስጥ ባሉት እና በሚኖሩት [ለ]ተንኮል እና አላማዎች ምክንያት፣ በራዕይ ይህን የጥበብ ቃል ለእናንተ በመስጠት አስጠንቅቄአችኋለሁ፣ እናም ጥንቱንም አስቀድሜ [ሐ]አስጠንነቅቄአችኋለሁ

፭ በመካከላችሁ ማንም ሰው [ሀ]ወይን ወይም የሚያሰክር መጠጥ የሚጠጣ ቢሆን፣ በፊቱ ቅዱስ ቁርባናችሁን ታቀርቡ ዘንድ በተሰባሰባችሁበት ጊዜ ብቻ ካልሆነ በስተቀር፣ እነሆ ይህ መልካም አይደለም፣ በአባታችሁም ፊት ተቀባይነት አይኖረውም።

፮ እናም፣ እነሆ፣ ይህም የወይን ጠጅ፣ አዎን፣ ከወይን ፍሬ በራሳችሁ የተሰራ ንጹህ [ሀ]ወይን ይሁን።

፯ ደግሞም፣ [ሀ]የሚያሰክር መጠጥ፣ ሰውነትን ለማጠብ እንጂ፣ ለሆድ አይደለም።

፰ እና ዳግም፣ ትምባሆ [ሀ]ለሰውነት፣ ወይም ለሆድ አይደለም፣ እና ለሰውም መልካም አይደለም፣ ነገር ግን በማመዛዘን እና በጥበብ ቢጠቀሚቸው፣ ለብልዝነት እና ለታመሙ ከብቶች የመድሀኒት ቅጠላት ናቸው።

፱ ደግሞም፣ ትኩስ መጠጦችም ለሰውነት እና ለሆድ አይደሉም።

፲ እናም ደግሞ እውነት እላችኋለሁ፤ ሁሉንም መልካም የሆኑትን [ሀ]ቅጠላ ቅጠል እግዚአብሔር ለሰውነት፤ ለፍጥረት እና ለሰው ጥቅም ይሆኑ ዘንድ መድቧቸዋልና—

፲፩ እያንዳንዶቹን ቅጠላ ቅጠል ሁሉ በወቅታቸው፤ ፍራፍሬዎችም ሁሉ በወቅታቸው መድቧቸዋል፤ እነዚህን ሁሉ በብልሃት እና [ሀ]በምስጋና ይጠቀሟቸው ዘንድ ነው።

፲፪ አዎን፣ [ሀ]የእንስሳትና የሰማይ አዕዋፋትንም [ለ]ስጋ፣ እኔ ጌታ ለሰው በምስጋና ጥቅም መድቤአቸዋለሁ፤ ነገር ግን እነዚህን [ሐ]እያሰለሱ ይጠቀሟቸው፤

፲፫ እና በክረምት ወይም በብርድ ወይም በረሀብ ጊዜያት ብቻ እንጂ፣ ይህን የማይጠቀሙበት ቢሆን የሚያስደስተኝ ነው።

፲፬ እና [ሀ]እህልም ለሰው እና ለእንስሳት ጥቅም፣ ለህይወት ሀይል፣ የተመደበ ነው፣ ለሰው ብቻ ሳይሆን ለምድር አራዊትና ለሰማይ አዕዋፋት፣ እና በምድር ላይ የሚሮጡት እና ለሚርመሰመሱት ለዱር እንስሳት ነው፤

፲፭ እና እነዚህንም በድርቅ እና በከፍተኛ የረሀብ ጊዜያት ይሆኑ ዘንድ ብቻ ለሰው ጥቅም እግዚአብሔር እነዚህንም ሰራ።

፲፮ የወይን ፍሬም፤ በምድር ውስጥ ወይም ከምድር በላይ ፍሬ የሚያመጣውም እንደሆነው፣ ሁሉም እህል ለሰው ምግብ ጥሩ ነው—

፲፯ ይህም ቢሆን፣ ስንዴ ለሰው፣ በቆሎ ለበሬ፣ እና አጃ ለፈረስ፣ እና አጃ ለአዕ

፪ሀ ት. እና ቃ. ፳፱፥፴፬።
ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ትእዛዛት።
፫ሀ ት. እና ቃ. ፹፱፥፲፰–፳፩።
ለ ቅ.መ.መ. ቅዱሳን።
፬ሀ ቅ.መ.መ. የሚስጥር ስብሰባ።
ለ ቅ.መ.መ. ሽንገላ (ውሸት)፣ መዋሸት፣ ማታለል።
ሐ ቅ.መ.መ. ማስጠንቀቅ፣ ማስጠንቀቂያ።
፭ሀ ዘሌዋ. ፲፥፱–፲፩፤
ኢሳ. ፭፥፲፩–፲፪፤
፩ ቆሮ. ፮፥፲።
፮ሀ ት. እና ቃ. ፳፯፥፩–፬።
፯ሀ ምሳ. ፳፥፩፤ ፳፫፥፳፱–፴፭።
፰ሀ ፩ ቆሮ. ፫፥፲፮–፲፯።
ቅ.መ.መ. ሰውነት።
፲ሀ ይህም አትክልቶች ማለት ነው። ዘፍጥ. ፩፥፳፱፤
ት. እና ቃ. ፶፱፥፲፯–፳።
፲፩ሀ ቅ.መ.መ. አመስጋኝ፣ ምስጋናን፣ ምስጋና መስጠት።
፲፪ሀ ፩ ጢሞ. ፬፥፫–፬፤
ት. እና ቃ. ፵፱፥፲፰–፳፩።
ለ ዘፍጥ. ፱፥፫፤
ዘሌዋ. ፲፩፥፩–፰።
ሐ ት. እና ቃ. ፶፱፥፳።
፲፬ሀ ዳን. ፩፥፮–፳።

ዋፋት እና ለአሳማ፣ እና ለምድር አራዊት ሁሉ፣ እና ገብስ፣ እንደ ሌላ እህልም፣ ለጠቃሚ እንስሳቶች ሁሉ፣ እና ለለስላሳ መጠጥ።

፲፰ እና ትእዛዛትን በማክበር፣ እነዚህን ነገሮች የሚጠብቁ እና ለማድረግ የሚያስታውሱ ቅዱሳን ሁሉ፣ ለስጋቸው ᵐፈውስ እና ለአጥንታቸው መጠገን ይቀበላሉ፤

፲፱ እናም ᵐጥበብ እና ታላቅ ᵃየእውቀት ሀብቶች፣ እንዲሁም የተሰወሩ ሀብቶች ንም ያገኛሉ፤

፳ እናም ᵐይሮጣሉ አይታክቱም፤ ይሄዳሉ አይደክሙም።

፳፩ እና እኔ ጌታ፣ አጥፊው መልአክ የእስራኤል ልጆችን እንዳለፋቸው፣ እነ ርሱን ᵐያልፋቸው ዘንድ እና እንዳይገድ ላቸውም ዘንድ፣ ᵃየተሰፋ ቃል እሰጣቸዋ ለሁ። አሜን።

ክፍል ፺

በመጋቢት ፰፣ ፲፰፻፴፫ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ ኦሀዮ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተሰጠ ራዕይ። ይህ ራዕይ የቀዳሚ አመራርን ለመመስረት የቀጠለ እርምጃ ነው (የክፍል ፹፮ ርዕስን ተመልከቱ)፤ በዚህም ምክንያት፣ የተጠቀሱት አማካሪዎች በመጋቢት ፲፰፣ ፲፰፻፴፫ (እ.አ.አ.) ተሾሙ።

፩–፫፣ የመንግስት ቁልፎች ለጆሴፍ ስሚዝ እና በእርሱም በኩል ለቤተክርስቲያኗ ተሰጥተዋል፤ ፬–፯፣ ስድኒ ሪግደን እና ፍሪድሪክ ጂ ዊሊያምስ በቀዳሚ አመራር ያገልግሉ፤ ፰–፲፩፣ ወንጌሉ ለእስራኤል ህዝብ፣ ለአህዛብ፣ እና ለአይሁድ፣ እያንዳንዱም ሰው በሚሰማው ቋንቋ ይሰበክለት፤ ፲፪–፲፰፣ ጆሴፍና አማካሪዎቹ ቤተክርስቲያኗን በስርዓት ያደራጁ፤ ፲፱–፳፯፣ የተለያዩ ግለሰቦች በቅንነት እንዲሄዱ እና በመንግስቱ እንዲያገለግሉ በጌታ ተመክረዋል።

፩ ጌታ እንዲህ ይላል፣ ልጄ ሆይ እውነት፣ እውነት እልሀለሁ፣ በልመናህ መሰረት፣ ኃጢአቶችህ ᵐተሰርየውልሀል፣ የአንተ እና የወንድሞችህ ጸሎቶች ወደ ጆሮዎቼ መጥ ተዋልና።

፪ ስለዚህ፣ የተሰጠህን የመንግስት ᵐቁልፎች ለመያዝ ከዚህ ጀምሮ ተባርከሀል፤ ይህም ᵃመንግስት ለመጨረሻ ጊዜ እየ መጣ ያለው ነው።

፫ እውነት እልሀለሁ፣ በዚህ አለምም ሆነ በሚመጣው አለም ሳለህ፣ የመንግስት ቁልፎች ከአንተ በምንም መንገድ አይወ ሰድብህም፤

፬ ይህም ቢሆን፣ አዎን፣ በአንተ በኩል ᵐየእግዚአብሔር ቃላት ለሌላ፣ እንዲሁም ለቤተክርስቲያኗ፣ ይሰጣሉ።

፭ እና የእግዚአብሔርን ቃላት የሚቀበሉ ሁሉ፣ እንደ ቀላል ነገር እንዳይቆጥሯቸው፣ እና በዚህም ፍርድ እንዳይመጣባቸው፣ እና ማእበሉ ሲወርድ፣ እና ነፋሱም ሲነፍስ፣ እና ᵐዝናብም ሲጥል፣ እና ቤታቸውንም ሲገፋው እንዳይደናቀፉ እና እንዳይወድቁ፣ እንዴት እንደሚይዟቸው ᵃይጠንቀቁ።

፲፰ ሀ ምሳ. ፫፡ ፰።
፲፱ ሀ ቅ.መ.መ. ጥበብ።
ለ ቅ.መ.መ. ምስክርነት፣ እውቀት።
፳ ሀ ኢሳ. ፵፡ ፴፩
፳፩ ሀ ዘፀአ. ፲፪፡ ፳፫፣ ፳፱።
ለ ት.እና ቃ. ፹፬፡ ፹።

፺ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. ይቅርታ ማድረግ።
፪ ሀ ት.እና ቃ. ፳፭፡ ፪።
ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
ለ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር መንግስት ወይም መንግስተ ሰማያት።
፬ ሀ የሐዋ. ፯፡ ፴፰፣ ሮሜ ፫፡ ፪፣ ዕብ. ፭፡ ፲፪፣ ት.እና ቃ. ፲፭፡ ፴፱፣ ፲፭፤ ቅ.መ.መ. ትንቢት፣ መተንበይ።
፭ ሀ ማቴ. ፣ ፡ ፳፤–፳፯።
ለ ት.እና ቃ. ፭፡ ፲፬።

፮ ደግሞም፣ ለወንድሞችህ ስድኒ ሪግ ደንና ፍረድሪክ ጂ ዊሊያም እውነት እላ ቸዋለሁ፣ ኃጢአቶቻቸውም ደግሞ ተሰ ርየዋል፣ እና የዚህን የመጨረሻ መንግስት ቁልፎችን መያዝን በተመለከተ ከአንተ ጋር እንደ እኩል ይቆጠራሉ፣

፯ ደግሞም እንዲደራጅ ያዘዝኩትን የነብ ያት ᵐትምህርት ቤት ማስተዳደሪያ ቁልፎ ችን መያዝን በተመለከተ ከአንተ ጋር እንደ እኩል ይቆጠራሉ፤

፰ በዚህም፣ የሚያምኑት ሁሉ፣ ለፅዮን፣ እና ለእስራኤል ህዝብ፣ እና ለአህዛብ ደህ ንነት በአገለግሎታቸው ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ፤

፱ በአገልግሎትህ ቃልን ይቀበሉ ዘንድ፣ እና በአገልግሎታቸውም ቃል፣ እስከ ምድር ዳርቻ ይሄድ ዘንድ፤ ᵐመጀመሪያ ወደ ᵃአህዛብ፣ እና ከዚያም እነሆ አስተ ውሉ፣ ወደ አይሁድም ይዞራሉ።

፲ ከዚያም ህዝብን፣ የአህዛብን አገሮች፣ ᵐየጆሴፍን ቤት፣ የደህንነታቸውን ወንጌል ለማሳመን የጌታ እጅ በሀይል ᵃየሚገለጥ በት ቀን ይመጣል።

፲፩ በዚያም ቀን እንዲህ ይሆናል፣ የወ ንጌል ሙላትን ለዚህ ᵐሀይል ᵃበተሾሙት በኩል፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ራዕይ በሚፈ ስባቸው ᵐበአፅናኙ አገልግሎት፣ እያንዳ ንዱ ሰው በገዛ ልሳን እና በራሱ ቋንቋ ᵐይሰ ማል።

፲፪ አሁንም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ᵐበአ ገልግሎቱ እና በአመራሩ እንድትቀጥሉ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ።

፲፫ እና የነቢያትን ትርጉም ስትጨርሱ፣ ከዚህ በኋላ የቤተክርስቲያኗን እና ᵐየትም ህርት ቤቱን ጉዳዮች ᵃትመራላችሁ፤

፲፬ እና ከጊዜ ወደ ጊዜም፣ በአፅናኙ እን ደሚገለጸው፣ ተነግረው የማይታወቁ የመ ንግስትን ᵐሚስጥራት ᵃበራዕይ ተቀበሉ፤

፲፭ እና ቤተክርስቲያኖችንም በስርዓት አደራጁ፣ እና ᵐአጥኑና ᵃተማሩ፣ እና ሁሉ ንም መልካም መጻህፍት፣ ᵐቋንቋዎች፣ ልሳኖች፣ እና ህዝብን እወቁ።

፲፮ እና ይህም፣ ኮሚቴውን መምራት፣ እና የዚህን ቤተክርስቲያን እና መንግስት ጉዳዮች በስርዓት ማደራጀት፣ በህይወ ታችሁ ሁሉ ጉዳያችሁ እና ተልዕኮአችሁ ይሆናል።

፲፯ ᵐአትፈሩ፣ ወይም አትዋረዱ፤ ነገር ግን በትዕቢታችሁ እና ᵃበኩራታችሁም ተገሰጹ፣ በነፍሶቻችሁ ወጥመድ ያመጣ ልና።

፲፰ ቤቶቻችሁንም በስርዓት አስተካክሉ፤ ᵐስራ ፈትነትን እና ᵃጽዱ አለመሆንን ከእ ናንተ አርቁ።

፲፱ አሁን፣ እውነት እልሀለሁ፣ ወድያ ውኑ ሲቻል፣ ለአማካሪህ እና ለጸሀፊህ፣ እንዲሁም ለፍረድሪክ ጂ ዊሊያምስ ቤተ ሰብ ስፍራ ይሰጥ።

፳ እና አዛውንቱ አገልጋዬ፣ ᵐጆሴፍ ስሚዝ፣ ቀዳማዊም፣ አሁን በሚኖርበት ስፍራ ከቤተሰቡ ጋር ይቀጥል፤ እና የጌታ አንደበት እስከሚወስንበትም ድረስ አይ ሸጥ።

፳፩ እና አማካሪዬ፣ እንዲሁም ᵐስድኒ

፯ ᵐ ቅ.መ.መ. የነቢያት ትምህርት ቤት።
፱ ᵐ ማቴ. ፲፱፡፴፣ ፴፣ ኤተር ፲፫፡፲–፲፪።
ᵃ ፩ ኔፊ ፲፫፡ ፵፪፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡ ፴፫፣ ፲፰፣ ፴፡ ።
፲ ᵐ ዘፍጥ. ፵፱፡ ፳፱–፳፯፣ ፩ ኔፊ ፲፭፡ ፲፣–፲፱።
ᵃ ት. እና ቃ. ፵፫፡ ፳፣–፳፯፣ ፹፰፡ ፹፣ ፹፯–፹፪።
፲፩ ᵐ ቅ.መ.መ. ክህነት።
ᵃ ቅ.መ.መ. መሾም፣ ሹመት፣ ጥሪ፣ በእግዚአብሔር መጠራት፣ የተጠራበት።
ᵃ ቅ.መ.መ. አፅናኝ።
ᵐ ቅ.መ.መ. የሚስዮን ስራ።
፲፪ ᵐ ቅ.መ.መ. አገልግሎት።
፲፫ ᵐ ቅ.መ.መ. የነቢያት ትምህርት ቤት።
ᵃ ት. እና ቃ. ፲፯፡ ፲፩–፲፪።
፲፬ ᵐ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ሚስጥሮች።
ᵃ ቅ.መ.መ. ራዕይ።
፲፭ ᵐ ት. እና ቃ. ፹፡ ፷፯፣ ፹፡ ፣ ፹፡ ፷፯፣ ፹፫፡ ፹፫።
ᵃ ት. እና ቃ. ፲፯፡ ፲፱–፲፡ ፣ ፲፡ ፷–፲፱።
ᵃ ቅ.መ.መ. ቋንቋ።
፲፯ ᵐ ሮሜ ፩፡ ፲፯፣ ፪ ኔፊ ፯፡ ፲፫።
ᵃ ት. እና ቃ. ፹፡ ፷፡ ፲፯፩።
ᵐ ቅ.መ.መ. ኩራት።
፲፰ ᵐ ት. እና ቃ. ፶፯፡ ፳፯–፳፱።
ᵐ ቅ.መ.መ. ስራ ሰልቺ፣ ስራ ፈቺ።
ᵃ ት. እና ቃ. ፴፯፡ ፴፪።
፳ ᵐ ቅ.መ.መ. ስሚዝ፣ ጆሴፍ ቀዳማዊ።
፳፩ ᵐ ቅ.መ.መ. ሪግደን፣ ስድኒ።

ሪግደን፣ የጌታ አንደበት እስከሚወስንበት ድረስ አሁን በሚኖርበት ይቆይ።

፳፩ እና ኤጲስ ቆጶሱ በቅንነት [ሀ]ወኪልን ለማግኘት ይፈልግ፣ እና ይህም ሰው [ለ]ሀብት ያከማቸ፣ የእግዚአብሔር ሰው፣ እና ጠንካራ እምነት ያለው ይሁን—

፳፪ በዚህም እያንዳንዱን እዳ ለመክፈል ችሎታ ይኖረው ዘንድ፤ የጌታ ጎተራ በሰዎቹ አይኖች ፊት መጥፎ ስም አይኖረው ዘንድ ወኪሉ ሀብት ያከማቸ የእግዚአብሔር ሰው፣ እና ጠንካራ እምነት ያለው ይሁን።

፳፫ [ሀ]ተግታችሁ ፈልጉ፣ ዘወትር [ለ]ጸልዩ፣ እናም እመኑ፣ እና በቅንነት ከተራመዳችሁ እና እርስ በራስ ቃል ኪዳን የገባችሁበትን [ሐ]ቃል ኪዳን ካስታወሳችሁ፣ [መ]ሁሉም ነገሮች ለእናንተ በጎነት አብረው ይሰራሉ።

፳፭ [ሀ]ቤተሰቦቻችሁ አነስተኛ ይሁኑ፤ በተለይም የቤተሰባችሁ አባል ያልሆኑትን በሚመለከት፤ በተለይም የአዛውንቱ ጆሴፍ ስሚዝ፣ ቀዳማዊ ቤተሰብም፤

፳፮ ስራዎቹ እንዲከናወኑ፣ ለእናንተ የተሰጧችሁ ነገሮች ከእናንተ እንዳይወሰዱ እና ብቁ ላልሆኑት እንዳይሰጥ ዘንድ—

፳፯ እና በዚህም ያዘዝኳችሁን ነገሮች ለማከናወን እንዳትደናቀፉ ቤተሰቦቻችሁ አነስተኛ ይሁኑ።

፳፰ ደግሜ፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ባሪያዬ ቪየና ዣክ ወጪዋን እንድትችል፣ እና ወደ ፅዮን ምድር ለመሄድ ገንዘብ ይሰጣት ዘንድ ፍቃዴ ነው፤

፳፱ እና የሚቀረው ገንዘብም ለእኔ ይቀደስ፣ እና በጊዜዬም ዋጋዋን ታገኛለች።

፴ እውነት እላችኋለሁ፣ ወደ ፅዮን ምድር እንድትሄድ፣ እና ከኤጲስ ቆጶስ እጅ ውርሷን እንድትቀበል ፍቃዴ ነው፤

፴፩ ታማኝ እስከሆነች ድረስ በሰላም እንድትሰፍር፣ እና ከዚህ በኋላ በቀኖቿ ስራ ፈት እንዳትሆን ፍቃዴ ነው።

፴፪ እነሆም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ይህን ትእዛዝ ጻፉ፣ እና በፅዮን ውስጥ ያሉ ወንድሞቻችሁን፣ በፍቅር ሰላምታ፣ በጊዜዬ በፅዮን [ሀ]እንድትመሩ እንደተጠራችሁ ንገሯቸው።

፴፫ ስለዚህ፣ በዚህ ጉዳይ እኔን ማድከማቸውን ያቁሙ።

፴፬ እነሆ፣ እላችኋለሁ በፅዮን ያሉት ወንድሞቻችሁ ንስሀ ይግቡ፣ እና መላእክት በእነርሱ ይደሰቱ።

፴፭ ይህም ቢሆን፣ በብዙ ነገሮች አልተደሰትኩም፤ እና በአገልጋዬ [ሀ]ዊሊያም ኢ መክሌይን፣ ወይም በአገልጋዬ ስድኒ ጊልበርት አልተደሰትኩም፤ እና ኤጲስ ቆጶሱና ሌሎች ንስሀ የሚገቡበት ብዙ ነገሮች አላቸው።

፴፮ ነገር ግን እውነት እላችኋለሁ እኔ ጌታ [ሀ]ከፅዮን ጋር እጣላለሁ፣ እና ጠንካራዋን ለምኛለሁ፣ እና እስክትሸነፍ እና በፊቴ [ለ]ንጹህ እስክትሆን ድረስ [ሐ]እገስጻለሁ።

፴፯ ከስፍራዋ ልትነቃነቅ አትችልምና። እኔ ጌታ ተናግሬዋለሁ። አሜን።

ክፍል ፶፩

በመጋቢት ፴፣ ፲፰፻፳፫ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ ኦሀዮ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ነቢዩ በዚህ ጊዜ ብሉይ ኪዳንን በመተርጎም ላይ ነበር። አፖ

፳፪ *ሀ* ት. እና ቃ. ፹፬፡ ፹፲፪–፹፲፫።
ለ ያዕቆ. ፪፡ ፲፯–፲፱።
፳፬ *ሀ* ቅ.መ.መ. ትጋት።
ለ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
ሐ ቅ.መ.መ. ቃል ኪዳን።
መ ዕዝ. ፰፡ ፳፪፤ ሮሜ ፰፡ ፳፰፰፤ ት. እና ቃ. ፲፡ ፲፭፤ ፹፳፪፡ ፯–፰።
፳፭ *ሀ* ይህም ጆሴፍ ስሚዝ ቀዳማዊ ይንከባከባቸው የነበሩ ደሆች ማለት ነው።
፴፪ *ሀ* ት. እና ቃ. ፹፯፡ ፻፲–፻፲፪።
፴፭ *ሀ* ት. እና ቃ. ፳፯፡ ፩፤ ፷፫፡ ፲–፲፱።
፴፮ *ሀ* ቅ.መ.መ. ፅዮን።
ለ ቅ.መ.መ. ንጹህ፣ ንጹህነት።
ሐ ቅ.መ.መ. መገሰጽ፣ ተግሳጽ።

ክርፋ በሚባለው የጥንት ፅሁፎች ክፍል ላይ ሲደርስ፣ ጌታን ጠየቀ እና ይህን መመሪያ ተቀበለ።

፩–፫፣ አፖክርፋው በትክክል የተተረጎመ ነው ነገር ግን በውስጡ በሰዎች እጆች እውነት ያልሆኑ ብዙ ተጨማሪዎች ነገሮችን ይይዛል፤ ፬–፯፣ ይህም መንፈስ የበራላቸውን ይጠቅማል።

፩ በእውነት፣ ጌታ [ሀ]አፖክርፋን በሚመለከት እንዲህ ይላል—በውስጡ እውነት የሆኑ አያሌ ነገሮችን ይዟል፣ እና አብዛኛውም በትክክል የተተረጎመ ነው፤

፪ በውስጡ፣ በሰዎች እጆች የተጨመሩ፣ እውነት ያልሆኑ ብዙ ነገሮችም አሉ።

፫ እውነት እላችኋለሁ፣ አፖክርፋው መተርጎሙ አስፈላጊ አይደለም።

፬ ስለዚህ፣ የሚያነበው፣ [ለ]ይረዳው፣ መንፈስ እውነትን ይገልጣልና፤

፭ እና [ሐ]መንፈስ ያበራለት እርሱም ከዚህ ጥቅም ያገኛል፤

፮ እና በመንፈስ የማይቀበለውም፣ አይ ጠቀምበትም። ስለዚህ መተርጎሙ አስፈላጊ አይደለም። አሜን።

ክፍል ፯፪

በመጋቢት ፲፭፣ ፲፰፻፴፫ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ ኦሀዮ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ራዕዩ በቅርብ ለጆሴፍ ስሚዝ እንደ አማካሪ ለተመደበው ለፍረድሪክ ጂ ዊሊያምስ በትብብር ድርጅት ውስጥ ስላለው ሀላፊነት መመሪያ የሚሰጥ ነው (ክፍሎች ፭፰ እና ፹፪ ርዕሶችን ተመልከቱ)።

፩–፪፣ ጌታ በትብብር ስርዓት ውስጥ አባል ስለመሆን ትእዛዝ ሰጥቷል።

፩ በእውነት ጌታ እንዲህ ይላል፣ ከዚህ አስቀድሞ በተሰጠው ትእዛዝ አማካይነት ለተደራጀው [ሀ]የትብብር ስርዓት ስለአገልጋዬ ፍረድሪክ ጂ ዊሊያምስ፣ በስርዓቱ እንድትቀበሉት ዘንድ፣ ራዕይ እና ትእዛዝ ሰጥቻችኋለሁ። ለአንዱ የምለው ለሁሉም እንዲሁ እላለሁ።

፪ ደግሞም፣ ለአገልጋዬ ፍረድሪክ ጂ ዊሊያምስ እላለሁ፣ የዚህ ስርዓት ተሳታፊ አባል ሁን፤ እና የበፊቱን ትእዛዛት በማክበር ታማኝ እስከሆንክ ድረስ ለዘለአለም ትባረካለህ። አሜን።

ክፍል ፯፫

በግንቦት ፯፣ ፲፰፻፴፫ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ ኦሀዮ ውስጥ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ።

፩–፭፣ ታማኝ የሆኑ ሁሉ ጌታን ያያሉ፤ ፮–፲፰፣ የእግዚአብሔር ልጅ የአብን ክብር በሙላት እስከሚቀበል ድረስ ከጸጋ ወደ ጸጋ እንደሄደ ዮሐንስ መሰከረ፤ ፲፱–፳፣

፯፩ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. አፖክርፋ።
፪ ሀ ቅ.መ.መ. ማስተዋል።
፭ ሀ ቅ.መ.መ. መነሳሻ፣ መነሳሳት፤ መንፈስ ቅዱስ።
፯፪ ፩ ሀ ት. እና ቃ. ፹፪፡ ፲፩፣ ፲፭–፳፩፡ ፪ ቅ.መ.መ. የትብብር ስርዓት።

ታማኝ ሰዎች፣ ከጻጋ ወደ ጻጋ በመሄድ ሙሉነቱን ደግመው መቀበል ይችላሉ፤ ፳፩–፳፪፣ በክርስቶስ በኩል የተወለዱትም የበኩር ቤተክርስቲያን ናቸው፤ ፳፫–፳፰፣ ክርስቶስ የእውነትን ሁሉ ሙላት ተቀበለ፣ እና ሰውም በታዛዥነት ይህንኑ ሊያደርግ ይችላል፤ ፳፱–፴፪፣ ሰው በመጀመሪያም ከእግዚአብሔር ጋር ነበር፤ ፴፫–፴፭፣ ንጥረ-ነገሮች ዘለአለማዊ ናቸው፣ እና ሰው የደስታን ሙላት በትንሳኤ ሊቀበል ይችላል፤ ፴፮–፴፯፣ የእግዚአብሔር ክብር የመረዳት ችሎታ ነው፤ ፴፰–፴፣ በክርስቶስ ቤዛነት ምክንያት ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ንጹሀን ናቸው፤ ፴፩–፴፫፣ መሪ ወንድሞች ቤተሰቦቻቸውን በስርዓት እንዲያደራጁ ታዘዙ።

፩ በእውነት፣ ጌታ እንዲህ ይላል፥ [ሀ]ኃጢ አቶቹን የሚተውና ወደ እኔ የሚመጣ፣ እና ስሜን [ለ]የሚጠራ፣ እና ድምጼን [ሐ]የሚያከ ብር፣ እና ትእዛዛቴን የሚያከብር እያንዳ ንዱ ነፍስ ሁሉ [መ]ፊቴን [ሠ]የሚያይበት እና እኔ እንደሆንኩም የሚያውቅበት ጊዜ ይመ ጣል፤

፪ እና እኔ ወደ አለም ለሚመጣ ለእያን ዳንዱ ሰው ሁሉ የማበራ የእውነት [ሀ]ብር ሀን ነኝ፤

፫ እኔ በአብ [ሀ]እንዳለሁ አብም በእኔ ነው እናም አብና እኔም አንድ ነን—

፬ ሙላቱን [ሀ]ስለሰጠኝ አብ ነኝ፣ እና በአ ለም ውስጥ ስለነበርኩና [ለ]ስጋንም ድንኳኔ ስላደረግሁ፣ እና በሰውም ልጆች መካከል ስለኖርኩ ወልድ ነኝ።

፭ በአለም ውስጥ ነበርኩ እና አባቴንም ተቀበልኩኝ፣ እና [ሀ]ስራዎቹም በግልፅ የታዩ ነበሩ።

፮ እና [ሀ]ዮሐንስ አየና [ለ]ስለክብሬ ሙላት መሰከረ፣ እና [ሐ]የዮሐንስ ሙሉ ምስክር ከዚህ በኋላ ይገለጣል።

፯ እናም እንዲህ በማለትም መሰከረ፥ ክብሩን፣ አለም ከመሆኗ በፊት [ሀ]ከመጀ መሪያ ጀምሮ እንደነበረ አየሁ፤

፰ ስለዚህ፣ በመጀመሪያው [ሀ]ቃል ነበር፣ እርሱም ቃል፣ እንዲሁም የደህንነት መላ እክተኛ ነበርና—

፱ የአለም [ሀ]ብርሀን እና [ለ]አዳኝ፤ አለም በእርሱ ሆኗልና፣ እና በእርሱም ውስጥ የሰ ዎች ህይወት እና የሰዎች ብርሀን ነበር፣ ወደ አለምም የመጣ የእውነት መንፈስ እርሱ ነውና።

፲ አለማት በእርሱ [ሀ]ሆነዋልና፤ ሰዎችም በእርሱ ተፈጥረዋል፤ ሁሉም ነገሮች በእ ርሱ፣ በእርሱም አማካይነት፣ እና ከእርሱ ሆነዋል።

፲፩ እና እኔ ዮሐንስ ክብሩን፣ በጸጋ እና በእውነት፣ እንዲሁም በመጣው እና በስ ጋም በኖረው፣ እና በመካከላችን በኖ ረው፣ በእውነት መንፈስ ተሞልቶ፣ እንደ አብ አንድያ ልጅ ክብሩን እንዳየሁ እመ ሰክራለሁ።

፶፫ ፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. መጸጸት፣ ንስሀ መግባት፣ ብቁ፣ ብቁነት።
ለ ኢዩ. ፪፡ ፴፪።
ሐ ቅ.መ.መ. ታዛዥነት፣ ታዛዥ፣ መታዘዝ።
መ ጆ.ስ.ት. ፩ ዮሐ. ፬፡ ፲፪ (ተጨማሪ)።
ሠ ዘፀአ. ፴፫፡ ፲፩፣ ት. እና ቃ. ፴፯፡ ፯–፰፣ ፰፯፡ ፲–፲፪፣ ፹፰፡ ፰፰፣ ፹፱፡ ፰፩፣ ፹፭፡ ፰፫፣ ፹፮፡ ፲፡ ቅ.መ.መ. አፅናኝ።
፪ *ሀ* ዮሐ. ፩፡ ፬–፱፣ ት. እና ቃ. ፲፬፡ ፱፣ ፲፭፡ ፲–፲፪፣ ፲፮፡ ፲፫–፲፭፣ ፲፯፡ ፲–፲፪፣ ፹፡ ፲፡ ፲፡ ኔፊ ፩፡ ፲፪–፲፬፣ ኤተር ፫፡ ፲፬–፲፯።
፫ *ሀ* ዮሐ. ፫፡ ፴፯፣ ፲፡ ፳፫፣ ፲፬፡ ፲–፲፪።
፬ *ሀ* ዮሐ. ፭፡ ፳፬፡ ፲፡ ቅ.መ.መ. ብርሀን፣ የክርስቶስ ብርሀን።
፫ *ሀ* ዮሐ. ፲፡ ፳፫–፳፰፣ ፲፯፡ ፳–፳፫፣ ት. እና ቃ. ፶፡ ፶፣ ፶፭–፶፭።
፬ *ሀ* ሞዛያ ፲፫፡ ፩–፯። ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—ስልጣን።
ለ ሉቃ. ፩፡ ፳፯–፴፫፣ ፪፡ ፬–፲፬፣ ፫ ኔፊ ፩፡ ፲፪–፲፬፣ ኤተር ፫፡ ፲፬–፲፯።
፭ *ሀ* ዮሐ. ፭፡ ፴፯፣ ፲፡ ፳፭፣ ፲፬፡ ፲–፲፪።
፮ *ሀ* ዮሐ. ፩፡ ፴፬።
ለ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—የክርስቶስ ክብር።
ሐ ዮሐ. ፳፡ ፴–፴፩።
፯ *ሀ* ዮሐ. ፩፡ ፩–፫፣ ፲፡ ፣ ፲፯፡ ፭፣ ት. እና ቃ. ፫፯፡ ፴፱።
፰ *ሀ* ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ያህዌህ።
፱ *ሀ* ቅ.መ.መ. ብርሀን፣ የክርስቶስ ብርሀን።
ለ ቅ.መ.መ. መድኃኒት።
፲ *ሀ* ዕብ. ፩፡ ፩–፫፣ ት. እና ቃ. ፫፯፡ ፳፱፣ ሙሴ ፩፡ ፴፩–፴፫።

፲፪ እና እኔ ዮሐንስ በመጀመሪያ ᵐሙላ
ትን እንዳልተቀበለ፣ ነገር ግን ᵃበጸጋ ላይ
ጸጋን እንደተቀበለ አየሁ፤
፲፫ እና ሙላትን በመጀመሪያ አልተቀ
በለም፣ ነገር ግን ሙላትን እስከሚቀበል
ድረስ ᵐከጸጋ ወደ ጸጋ ቀጠለ፤
፲፬ እና ሙላትን በመጀመሪያ ስላልተቀ
በለ፣ በዚህም ᵐየእግዚአብሔር ልጅ ተብሎ
ተጠርቷል።
፲፭ እና እኔ ᵐዮሐንስ እመሰክራለሁ እና
አስተውሉ፣ ሰማያት ተከፈቱ ᵃመንፈስ
ቅዱስ በእርሱ ላይም ᵇበርግብ አምሳል
ወረደ፣ እናም አረፈበት፣ እና ድምፅ ከሰ
ማያት መጥቶ በእርሱ ደስ የሚለኝ ᶜየም
ወደው ልጄ ይህ ነው አለ።
፲፮ እና እኔ ዮሐንስ እርሱ የአብን ክብር
በሙላት እንደተቀበለ እመሰክራለሁ፤
፲፯ እና ᵐሀይልን ᵃሁሉ፣ በሰማይ እና በም
ድር ላይ ተቀበለ፣ እና ᵇየአብ ክብርም ከእ
ርሱ ጋር ነበር፣ በእርሱ ውስጥም ይኖራልና።
፲፰ እና እንዲህም ይሆናል፣ እናንት
ታማኝ ብትሆኑ የዮሐንስን ምስክር በሙ
ላት ትቀበላላችሁና።
፲፱ እነዚህን አባባል የምሰጣችሁ እንድት
ረዱ እና እንዴት እንደምታመልኩ እንድ
ታውቁ፣ እና ምን ᵐእንደምታመልኩ እን
ድታውቁ፣ በስሜ ወደ አብ እንድትመጡ፣
እና በጊዜም ሙላትን ትቀበሉ ዘንድ ነው።
፳ ᵐትእዛዛቴን የምታከብሩ ከሆናችሁም
ᵃሙላቱን ትቀበላላችሁና፣ እና እኔ በአብ
እንደሆንኩ እናንት በእኔ ᵇትከብራላችሁ፤
ስለዚህ፣ እላችኋለሁ፣ ᶜበጸጋ ላይ ጸጋን
ትቀበላላችሁ።
፳፩ አሁንም፣ እውነት እላችኋለሁ ᵐበመ
ጀመሪያም ከአብ ዘንድ ነበርኩኝ፣ እና
ᵃበኩርም ነኝ፤
፳፪ እና በእኔ የተወለዱትም የዚህ ᵐክብር
ᵃተካፋዮች ናቸው፣ እና የበኩር ቤተክርስ
ቲያንም ናቸው።
፳፫ አስቀድማችሁ ᵐከአብ ጋር የነበራ
ችሁ እናንተ መንፈስ፣ እንዲሁም የእው
ነት መንፈስ ነበራችሁ፤
፳፬ እና ነገሮች እንዳሉ፣ እንደነበሩ፣
እናም ወደፊት እንደሚሆኑ ᵐየሚታወቅ
በት ᵃእውነት ነው።
፳፭ እና ማንኛውም ከዚህ ᵐበላይ ወይም
በታች የሆነው ከክፉው መንፈስ ነው፣ እር
ሱም ከመጀመሪያ ᵃሀሰተኛ የነበረው ነው።
፳፮ ᵐየእውነት መንፈስም እግዚአብ
ሔር ነው። እኔ የእውነት መንፈስ ነኝ፣
እና ዮሐንስ ስለእኔ እንዲህ በማለት መስ
ክሯል፥ የእውነትን ሙላት፣ አዎን፣ እን
ዲሁም ሁሉንም እውነቶች ተቀበለ።
፳፯ እና ትእዛዛቱን ካላከበረ በስተቀር
ማንም ሰው ᵐሙላትን አይቀበልም።
፳፰ ትእዛዛቱን ᵐየሚያከብርም፣ በእውነት

፲፪ ᵐ ፊልጵ. ፪፡ ፣–፲፩።
ᵃ ዮሐ. ፩፡ ፲፯–፲፯።
፲፫ ᵐ ሉቃ. ፪፡ ፶፪።
፲፬ ᵐ ሉቃ. ፩፡ ፴፭–፴፯፤ ት. እና ቃ. ፣፡ ፳፩፤ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ—እግዚአብሔር ወልድ።
፲፭ ᵐ ዮሐ. ፩፡ ፳፱–፴፪።
ᵃ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
ᵇ ቅ.መ.መ. የርግብ መልእክት።
ᶜ ማቴ. ፫፡ ፲፯–፲፯።
፲፯ ᵐ ቅ.መ.መ. ሀይል፣ ኢየሱስ ክርስቶስ—ስልጣን።
ᵃ ማቴ. ፳፰፡ ፲፰፤ ዮሐ. ፲፯፡ ፪፤ ፩ ጴጥ. ፫፡ ፳፪።
ᵇ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ—እግዚአብሔር አብ።
፲፱ ᵐ ዮሐ. ፬፡ ፳፩–፳፯፤ ፲፯፡ ፫፤ የሐዋ. ፲፯፡ ፳፪–፳፰። ቅ.መ.መ. ማምለክ።
፳ ᵐ ት. እና ቃ. ፱፡ ፳፰።
ᵃ ዮሐ. ፩፡ ፲፯፤ ት. እና ቃ. ፹፡ ፱–፴፤ ፴፱።
ᵇ ዮሐ. ፲፯፡ ፬–፭፤ ፳፪። ቅ.መ.መ. ሰው፣ ሰዎች—የሰው እንደ እግዚአብሔር አይነት ለመሆን ያለው ችሎታ።
ᶜ ቅ.መ.መ. ጸጋ።
፳፩ ᵐ ዮሐ. ፩፡ ፩–፪፤ ፩ ጴጥ. ፩፡ ፲፱–፳፣ ሙሴ ፩፡ ፪።
ᵃ ቅ.መ.መ. በኩር።
፳፪ ᵐ ቅ.መ.መ. የሰለስቲያል ክብር።
ᵃ ፩ ጴጥ. ፭፡ ፩፤ ት. እና ቃ. ፻ወ፣፡ ፶፯።
፳፫ ᵐ ቅ.መ.መ. ሰው፣ ሰዎች—ሰው፣ የሰማይ አባት የመንፈስ ልጅ።
፳፬ ᵐ ቅ.መ.መ. እውቀት።
ᵃ ቅ.መ.መ. እውነት።
፳፭ ᵐ ት. እና ቃ. ፳፡ ፴፭።
ᵃ ዮሐ. ፰፡ ፵፬፤ ፪ ኔፊ ፪፡ ፲፰፣ ሙሴ ፩፡ ፩።
፳፮ ᵐ ዮሐ. ፲፡ ፣።
፳፯ ᵐ ቅ.መ.መ. ፍጹም።
፳፰ ᵐ ቅ.መ.መ. ታዛዥነት፣ ታዛዥ፣ መታዘዝ።

እና ሁሉንም ነገሮች ^በማወቅ እስከሚከበር ድረስ፣ እውነት እና ሓብርሀንን ይቀበላል።

፳፭ ሰው ደግሞ ᵛበመጀመሪያ ከእግዚ አብሔር ጋር ነበር። ^የመረዳት ችሎታ፣ ወይም የእውነት ብርሀን፣ የተፈጠረ ወይም የተሰራ አይደለም፣ በእርግጥም ሊሆን አይ ችልም።

፴ ሁሉም እውነት እግዚአብሔር ባስቀ መጣቸው ተፅዕኖ አካባቢያቸው፣ በራሳ ቸው ᵛየሚሰሩ፣ እንደየራሳቸው የመረዳት ችሎታ፣ ራሳቸውን የቻሉ ናቸው፤ አለበ ለዚያም ምንም አይኖርም።

፴፩ እነሆ፣ ይህ የሰው ᵛነጻ ምርጫ ነው፣ እና ይህ የሰው ኩነኔ ነው፤ ከመጀመሪያ የነ በረው ^በግልጽ ስለታየላቸው፣ እና ብርሀ ንንም አልተቀበሉትምና።

፴፪ እና መንፈሱ ᵛብርሀንን የማይቀበል በእርሱ በፍርድ ላይ ነው።

፴፫ ሰው ᵛመንፈስ ነውና። ^ንጥረ-ነገ ሮች ዘለአለማዊ ናቸው፣ እና መንፈስ እና ንጥረ-ነገር ሳይለያዩ የተያያዙ፣ የደስታን ሙላትን የሚቀበሉ ናቸው።

፴፬ እና ᵛሲለያዩም፣ ሰው ^የደስታን ሙላት አይቀበልም።

፴፭ ᵛንጥረ-ነገሮች የእግዚአብሔር ድን ኳን ናቸው፤ አዎን፣ ሰውም የእግዚአብ ሔር ድንኳን፣ እንዲሁም ^ቤተመቅደሳት፣ ነው፤ እና ቤተመቅደሱ የረከሰ ቢሆን፣ እግ ዚአብሔር ያንን ቤተመቅደስ ያፈርሰዋ ልና።

፴፮ የእግዚአብሔር ᵛክብር ^የመረዳት ችሎታ ነው፣ ወይም በሌላ ቃላት፣ ሓብር ሀንና እውነት ነው።

፴፯ ብርሀን እና እውነት ᵛክፉውን ይተ ዋል።

፴፰ እያንዳንዱ የሰው መንፈስ በመጀመ ሪያ ᵛየዋህ ነበር፤ እና እግዚአብሔር ሰውን ^ከውድቀቱ ^ሲያድን፣ ሰዎችም ዳግም በህጻንነት በእግዚአብሔር ፊት ᵛየዋህ ሆኑ።

፴፱ ክፉውም መጣ እና፣ ባለመታዘዝና በአባቶቻቸው ᵛባህል ምክንያት፣ ብርሀንን እና እውነትን ከሰዎች ልጆች ^ነጠቀ።

፵ ነገር ግን ᵛልጆቻችሁን በብርሀን እና በእውነት እንድታሳድጓቸው ዘንድ አዛች ኋለሁ።

፵፩ ነገር ግን አገልጋዬ ፍረድሪክ ጂ ዊሊያምስ እውነት እልሀለሁ፣ በዚህ ኩነኔ ቀጥለሀል፤

፵፪ በትእዛዛትም በኩል ልጆችህን ብርሀን እና እውነት ᵛአላስተማርክም፤ እና ክፉ ውም በአንተ ላይ ሀይል አለው፣ እና ይህም የስቃይህ ምክንያት ነው።

፳፯ *ለ* ዮሐ. ፲፯፡፲፡
ት. እና ቃ. ፹፯፡፵፱፡ ፳፯።
ሐ ት. እና ቃ. ፱፡ ፳፩፤
፹፩፡ ፵፳።
ቅ.መ.መ. ብርሀን፣
የክርስቶስ ብርሀን።
፳፱ *ሀ* አብር. ፫፡ ፲፳።
ቅ.መ.መ. ሰው፣ ሰዎች፤
ቅድመ ምድራዊ ህይወት።
ለ ቅ.መ.መ. እውቀተኛነት፣
እውቀተኛዎች።
፴ *ሀ* ፪ ኔፊ ፪፡ ፲፫–፳፯።
፴፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. ነጻ ምርጫ።
ለ ዘዳግ. ፴፡ ፲፩–፲፭፤
ት. እና ቃ. ፹፡ ፳፫–፳፭።
፴፪ *ሀ* ቅ.መ.መ. ብርሀን፣ የክርስቶስ
ብርሀን፤
እውነት።
፴፫ *ሀ* ት. እና ቃ. ፫፯፡ ፪፤
አብር. ፭፡ ፯–፳።
ቅ.መ.መ. ሰው፣ ሰዎች—
ሰው፣ የሰማይ አባት
የመንፈስ ልጅ።
ለ ት. እና ቃ. ፪፴፩፡ ፯–፳፤
፪፴፳፡ ፲፯።
ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
፴፬ *ሀ* ፪ ኔፊ ፱፡ ፳–፲።
ለ ቅ.መ.መ. ደስታ።
፴፭ *ሀ* ት. እና ቃ. ፪፴፡ ፳፪።
ለ ፩ ቆሮ. ፫፡ ፲፯–፲፯።
፴፮ *ሀ* ቅ.መ.መ. ኢየሱስ
ክርስቶስ—የክርስቶስ ክብር፣
ክብር።
ለ ት. እና ቃ. ፪፴፡ ፲፳–፲፱፤
አብር. ፫፡ ፲፱።
ቅ.መ.መ. እውቀተኛነት፣
እውቀተኛዎች።
ሐ ት. እና ቃ. ፹፳፡ ፯–፲፫።
፴፯ *ሀ* መ ሴ ፩፡ ፲፪–፲፯።
ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
፴፳ *ሀ* ቅ.መ.መ. የዋህ፣ የዋህነት።
ለ ቅ.መ.መ. የአዳም እና
የሔዋን ውድቀት።
ሐ ሞዛያ ፳፯፡ ፳፱–፳፯፤
ሙሴ ፩፡ ፱፤
ኢ.ኢ. ፩፡ ፫።
ቅ.መ.መ. ቤዛ፣
ማዳን፣ ቤዛነት።
መ ሞሮኒ ፰፡ ፰፣ ፲፪፣ ፳፪፤
ት. እና ቃ. ፳፱፡ ፴፯–፴፯።
ቅ.መ.መ. ደህንነት—
የልጆች ደህንነት።
፴፱ *ሀ* ሕዝ. ፳፡ ፲፰–፲፱፤
አልማ ፫፡ ፰።
ቅ.መ.መ. ባህል።
ለ ማቴ. ፲፫፡ ፲፰–፲፱፤
፪ ቆሮ. ፱፡ ፫–፱፤
አልማ ፲፪፡ ፱–፲፩።
፴ *ሀ* ቅ.መ.መ. ቤተሰብ—
የወላጆች ሀላፊነቶች።
፴፪ *ሀ* ፩ ሳሙ. ፫፡ ፲፩–፲፫፤
ት. እና ቃ. ፹፡ ፳፩–፴፩።

፯፫ አሁንም ትእዛዝ እሰጥሀለሁ—የም ትድን ቢሆን ቤትህን ᵐበስርዓት አደራጅ፣ በቤትህ ውስጥ አያሌ ትክክል ያልሆኑ ነገ ሮች አሉና።

፯፬ ለአገልጋዬ ስድኒ ሪግደን በእውነት እለዋለሁ፣ በአንዳንድ ነገሮች ልጆቹን በሚመለከት ትእዛዝን አላከበረም፤ ስለ ዚህ፣ አስቀድሞ ቤቱን በስርዓት ያደራጅ።

፯፭ በእውነት፣ ለአገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ ይህን እላለሁ፣ ወይም በሌላ ቃላት፣ ባልንጀሮቼ ብዬ እጠራችኋለሁ፣ እናንት ᵐባልንጀሮቼ ናችሁና፣ እና ከእኔም ጋር ውርስ ይኖራችኋል—

፯፮ ᵐአግልጋዮቼ ብዬ የምጠራችሁ በአ ለም ምክንያት ነው፣ እና እናንተም ለእ ነርሱ በእኔ ምክንያት አገልጋዮቻቸው ናችሁ—

፯፯ አሁንም፣ በእውነት ለአገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ እላለሁ—ትእዛዛትን አላከበርክም፣ እና በጌታ ፊትም ᵐተገስጸህ መቆም ያስፈልግሀል፤

፯፰ ᵐቤተሰብህ ንስሀ መግባትና አንዳንድ ነገሮችን መተው አለባቸው፣ እና የምትላቸ ውንም በቅንነት ማድመጥ ያስፈልጋቸዋል፣ ወይም ከስፍራቸው ይወጣሉ።

፯፱ ለአንዱ የምለው ለሁሉም እላለሁ፤ ዘወትር ᵐጸልዩ አለበለዚያም ክፉው በው ስጣችሁ ሀይል ይኖረዋል፣ እና ከስፍራችሁ ያስወጣችኋል።

፰ የቤተክርስቲያኔ ኤጲስ ቆጶስ፣ አገልጋዬ ኒውል ኬ ዊትኒም፣ ሊገሰፅ፣ እና ቤተሰቡን በስርዓት ሊያደራጅ፣ እና በቤትም በተጨ ማሪ ቅን እና አሳቢ እንዲሆኑ፣ እና ዘወት ርም እንዲጸልዩ ሊያደርግ ያስፈልገዋል፣ ወይም ᵐከስፍራቸው ይወጣሉ።

፰፩ ባልንጀሮቼ፣ አሁን እላችኋለሁ፣ አገ ልጋዬ ስድኒ ሪግደን በጉዞው ይሂድ፣ እና ይፍጠን፣ እና ደግሞም በምሰጠው የንግግር ችሎታ የጌታን ᵐየተወደደች አመትን፣ እና የደህንነትን ወንጌልን ያውጅ፤ እና በአንድ አላማ በምታደርጉት የእምነት ጸሎት እደ ግፈዋለሁ።

፰፪ እና አገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ፣ እና ፍረድሪክ ጂ ዊሊያምስም ይፍጠኑ፣ እና እንድ እምነት ጸሎታቸውም ይሰጣ ቸዋል፤ እና እኔ የምላችሁን እስከጠበቃ ችሁ ድረስ በዚህ አለምም፣ ሆነ በሚመ ጣው አለም አትሸነፉም።

፰፫ እና፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ቅዱስ መጻሕፍቴን ᵐለመተርጎም እንድትፈጥኑ፣ እና የታሪክ፣ እና የሀገሮች፣ እና የመንግ ስታት፣ የእግዚአብሔር እና የሰው ህግጋት ᵃእውቀትን ᵇእንድታገኙ ፍቃዴ ነው፣ ይህም ሁሉ ለፅዮን ደህንነት ነው። አሜን።

ክፍል ፯፬

በነሀሴ ፪፣ ፲፰፻፴፫ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ ኦሀዮ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተ ሰጠ ራዕይ። ሀይረም ስሚዝ፣ ሬኖልድስ ከሁን፣ እና ጄርድ ካርተር ለቤተክርስ ቲያን መገንባት በኮሚቴነት ተመድበዋል።

፩–፱፣ ጌታ ለቀዳሚ አመራር ስራ ስለሚ ገነባው ቤት የሚመለከት ትእዛዝ ሰጠ፤ ፣–፲፪፣ የማተሚያ ቤት ይገንባ፤ ፲፫–፲፯፣ ልዩ ውርሶች ተመድበዋል።

፯፫ *ሀ* ፩ ጢሞ. ፫፡፩–፭።
፯፭ *ሀ* ት. እና ቃ. ፯፬፡፳፫፣ ፳፫፡፳፰።
፯፮ *ሀ* ዘሌዋ. ፳፭፡፲፭፣ ፲፭፣ ፩ ኔፊ ፳፩፡፣–፳። ቅ.መ.መ. አገልግሎት።
፯፯ *ሀ* ት. እና ቃ. ፯፭፡፩–፪። ቅ.መ.መ. መገሰጽ፣ ተግሳጽ።
፯፰ *ሀ* ቅ.መ.መ. ቤተሰብ—የልጆች ሀላፊነቶች።
፯፱ *ሀ* ፣ ኔፊ ፲፰፡፲፩–፳፩።
፣ *ሀ* ት. እና ቃ. ፳፬፡ ፴።
፣፩ *ሀ* ሉቃ. ፪፡፲፱።
፣፣ *ሀ* ቅ.መ.መ. የጆሴፍ ስሚዝ ትርጉም (ጆ.ስ.ት.)።
ለ ቅ.መ.መ. እውቀት።
ሐ ት. እና ቃ. ፲፫፡ ፫፩–፲፣ ፲፲፡፳።

፩ ደግሞም፣ [ሀ]ባልንጀሮቼ እውነት እላች ኋለሁ፣ በዚህ በከርትላንድ ምድር ውስጥ፣ በቤቴ በመጀመር፣ የፅዮን [ለ]ካስማ ከተማን ጅማሬ መሰረት ለመጣል እና ለማዘጋጀት ትእዛዝን እሰጣችኋለሁ።

፪ እነሆም፣ በሰጠኋችሁ [ሐ]ምሳሌ መሰረት መደረግ አለበት።

፫ እና በደቡብ ያለው የመጀመሪያው ከፊል መሬት ለእኔ፣ ራዕዮችን ለሚቀበሉ በት ለአመራር ስራ፣ ለአመራር ቤት መሰ ሪያ ይቀደስ፤ እናም ይህም ቤተክርስቲያኗን እና መንግስቱን በሚመለከቱ ሁሉም ነገሮች [መ]ለአመራር አገልግሎት ስራ ነው።

፬ እውነት እላችኋለሁ፣ ይህም፣ በውስጠ ኛው አደባባይ፣ አስራ ሰባት ሜትር በሀያ ሜትር ስፋት እና ርዝመቱ ይሁን።

፭ እና፣ ከዚህ በኋላ በሚሰጣችሁ ንድፍ መሰረት፣ የታች አደባባይና የላይ አደባ ባይ ይኑረው።

፮ እና፣ በክህነት ስልጣን ስርዓት መሰ ረት፣ ከዚህ በኋላ በሚሰጣችሁ ንድፍ መሰ ረት፣ ይህ ከመሰረቱ ጀምሮ ለጌታ ይቀደስ።

፯ እና ይህም ለአመራር ስራ ለጌታ ሁሉ ይቀደስ።

፰ እና ማንኛውም [መ]እርኩስ ነገር ወደው ስጥ እንዲገባ አትፍቀዱ፤ እና [ሀ]ክብሬም በዚያ ይሆናል፣ እና በዚያም እገኛለሁ።

፱ ማንኛውም [መ]እርኩስ ነገር ቢገባበት ግን፣ ክብሬ በዚያ አይሆንም፤ እና ወደዚ ህም አልገባም።

፲ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ሁለ ተኛው ከፊሉ መሬት ለእኔ ቤት መሰሪያ፣ ለቅዱስ መጻሕፍቴ [መ]መታተምና [ለ]መተር ጎም ስራ፣ እና ለማዛችሁ ማንኛቸውም ነገ ሮች ሁሉ፣ ለእኔ ይቀደስ።

፲፩ እና ይህም፣ በውስጥ አደባባዩ፣ አስራ ሰባት ሜትር በሀያ ሜትር ስፋት እና ርዝመት ይሁን፤ እና የበታች እና የላይ አደባባይ ይኑረው።

፲፪ እና ይህም ቤት ከመሰረቱ ጀምሮ፣ ለህትመት ስራ፣ በሚሰጣችሁ ንድፍ መሰ ረት በሁሉም ነገሮች ቅዱስ እና ያልረከሰ እንዲሆን ማንኛቸውም በማዛችሁ ሁሉም ነገሮች ሁሉ ለጌታ ይቀደስ።

፲፫ እና በሶስተኛው ከፊል መሬት ላይ አገልጋዬ ሀይረም ስሚዝ ውርሱን ይቀ በል።

፲፬ እና በሰሜን ላይ ባለው በመጀመሪያው እና በሁለተኛው ከፊል ስፍራ ላይ አገልጋዬ ሬኖልድስ ከሁን እና ጀርድ ካርተር ውርሶ ቻቸውን ይቀበሉ—

፲፭ የመደብኩላቸውን ስራ ያከናውኑ ዘንድ፣ እኔ ጌታ በሰጠኋችሁ ትእዛዝ መሰ ረት የቤቶቹ የግንባታ ኮሚቴ ይሁኑ።

፲፮ እነዚህ ሁለት ቤቶች እነርሱን በሚ መለከት ትእዛዝ እስክሰጣችሁ ድረስ እን ዳይገነቡ።

፲፯ አሁንም በዚህ ጊዜ ምንም ተጨማሪ ነገርን አልሰጣችሁም። አሜን።

ክፍል ፶፭

በሰኔ ፩፣ ፲፰፻፴፫ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ ኦሀዮ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተ ሰጠ ራዕይ። ይህ ራዕይ የማምለኪያ እና የመማሪያ ቤት፣ በልዩም የጌታ ቤት፣ እንዲሰሩ ቀጣይ መለኮታዊ መመሪያ የተሰጠበት ነው (ክፍል ፴፰፡ ፲፰–፲፱–፲፴፤ ፻፲ን ተመልከቱ)።

፶ ፩ ሀ ት. እና ቃ. ፶፫፡ ፶፭። ለ ቅ.መ.መ. ካስማ።
፪ ሀ ት. እና ቃ. ፶፪፡ ፲፡–፲፭። ለ ፩ ነገሥ. ፰፡ ፲–፲፩። ቅ.መ.መ. ክብር።
፫ ሀ ት. እና ቃ. ፲፯፡ ፲፭–፲፮፤ ት. እና ቃ. ፲፱፡ ፲፮–፳። ለ ፩ ነገሥ. ፰፡ ፲–፲፩። ቅ.መ.መ. ክብር።
፬ ሀ ት. እና ቃ. ፶፯፡ ፲፭–፲፯። ለ ቅ.መ.መ. የጆሴፍ ስሚዝ ትርጉም (ጆ.ስ.ት.)።
፲ ሀ ት. እና ቃ. ፲፡ ፲፱–፳፡ ፳፩–፳፪።
፲፩ ሀ ት. እና ቃ. ፲፡ ፲–፲፭፤ ፳፡ ፳–፳፪።

፩–፯፣ ቅዱሳን የጌታን ቤት ለመስራት ባሳ ዩት ድክመት ይገሰጻሉ፤ ፰–፲፣ ጌታ ቤቱን በመጠቀም ህዝቡን ከላይ ሀይልን ሊያለብ ሳቸው ይፈልጋል፤ ፲፩–፲፯፣ ቤቱም የማ ምለኪያ ቦታ እና ለሐዋርያት ትምህርት ቤት እንዲሆን ይቀደስ።

፩ በእውነት ለምወዳችሁ ለእናንተ ጌታ እንዲህ ይላል፣ እና የምወዳቸውንም ኃጢአታቸውን [ሀ]ለመሰረይ [ለ]እገስጻቸዋ ለሁ፣ በቅጣትም [ሐ]ከፈተና በሁሉም ነገሮች [መ]የሚድኑበትን መንገድ አዘጋጃለሁና፣ እና ወድጃችኋለሁም—

፪ ስለዚህ፣ በፊቴ መቀጣት እና መገሰፅ ያስፈልጋችኋል፤

፫ [ሀ]ቤቴን ስለመገንባት የሰጠኋችሁን፣ ታላቅ ትእዛዝ በሁሉም ነገሮች ስላላሰባች ሁበት፣ አስከፊ የሆነን ኃጢአት በእኔ ላይ ሰርታችኋልና፤

፬ [ሀ]እንግዳ የሆነን ስራዬን አከናውን ዘንድ፣ በሁሉም ስጋ ለባሽ ላይ መንፈሴን [ለ]አፈስ ዘንድ፣ ሐዋሪያቴን ለመጨረሻ ጊዜ የወይኑ ስፍራዬን [ሐ]እንዲመለምሉ ለማዘጋ ጀት ያዘጋጀሁት ንድፍ ታላቅ ትእዛዝ በሁ ሉም ነገሮች አላሰባችሁበትም፤

፭ ነገር ግን እነሆ፣ እውነት እላችኋ ለሁ፣ በመካከላችሁ የጠራኋቸው የተሾሙ ብዙ አሉ ነገር ግን [ሀ]የተመረጡት ጥቂቶች ናቸው።

፮ ያልተመረጡትም በጣም አሳዛኝ ኃጢ አት ሰርተዋል፣ በዚያም በቀትርም ጊዜ [ሀ]በጨለማ ይሄዳሉ።

፯ እና ለዚህም ምክንያት [ሀ]ጾማችሁ እና ልቅሶአችሁ፣ ወደ [ለ]ፀባኦት ጌታ፣ ይህም ሲተረጎም የመጀመሪያው ቀን [ሐ]ፈጣሪ፣ የመጀመሪያው እና የመጨረሻው ወደሆ ነው፣ ወደ እርሱ ጆሮዎች ይመጡ ዘንድ [መ]የክብር ስብሰባችሁን እንድትጠሩ ትእዛ ዝን ሰጠችሁ።

፰ አዎን፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ቤትን ትገነቡ ዘንድ ትእዛዝ ሰጠኋችሁ፣ በዚህ ቤትም የመረጥኳቸውን ከላይ [ሀ]መንፈሳዊ ስጦታ ልሰጣችሁ አቅጃለሁ፤

፱ ይህም አብ ለእናንተ የሚገባው [ሀ]ቃል ኪዳን ነውና፤ ስለዚህ እንደ ኢየሩሳሌም ሐዋሪያቴ፣ እንድትቆዩ አዛችኋለሁ።

፲ ይህም ቢሆን፣ አገልጋዮቼ በጣም አሳዛኝ ኃጢአትን ሰርተዋል፤ እና በነቢ ያት [ሀ]ትምህርት ቤትም [ለ]አለመስማማት ተነስቷል፤ ይህም ለእኔ በጣም አሳዛኝ ነው ይላል ጌታ፤ ስለዚህ እንዲገሰጹ ላኳቸው።

፲፩ እውነት እላችኋለሁ፣ ቤትን እንድ ትገነቡ ፍቃዴ ነው። ትእዛዛቴን ብታከብሩ ይህን ለመገንባት ሀይል ይኖራችኋል።

፲፪ ትእዛዛቴን [ሀ]ካላከበራችሁ፣ የአብ [ለ]ፍቅር ከእናንተ ጋር አይቀጥልም፣ ስለ ዚህ በጭለማ ትሄዳላችሁ።

፲፫ አሁን ይህ ጥበብ፣ እና የጌታ አዕምሮ

፯ ፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. ይቅርታ
ማድረግ።
ለ ዘዳግ. ፲፩፡፩–፰፤
ምሳ. ፲፫፡፲፤
ዕብ. ፲፪፡፭–፲፩፤
ሐሌ. ፲፩፡፫፤
ት. እና ቃ. ፲፩፡፱–፲፡፭፤
፲፭፡፮፤
ቅ.መ.መ. መገሰጽ፣
ተግሳጽ።
ሐ ቅ.መ.መ. መፈተን፣ ፈተና።
መ ፩ ቆሮ. ፲፡፲፫።
፫ *ሀ* ሐጌ. ፩፡፮–፲፩፤
ት. እና ቃ. ፹፯፡፲–፲፲፱።
ቅ.መ.መ. ቤተመቅደስ፣
የጌታ ቤት።
፬ *ሀ* ኢሳ. ፭፯፡፭፩፤
ት. እና ቃ. ፲፩፡፲፮፡፲፭።
ለ ምሳ. ፩፡፳፫፣
ኢዩ. ፪፡፭፯፣
ት. እና ቃ. ፲፱፡፴፯።
ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ፣
የመንፈስ ስጦታዎች።
ሐ ያዕቆ. ፭፡፯–፡፡፭፤
ት. እና ቃ. ፭፬፡፲፱፤
፴፫፡፫–፴።
ቅ.መ.መ. የጌታ የወይን
አትክልት ስፍራ።
፭ *ሀ* ማቴ. ፭፡፲፤
ት. እና ቃ. ፲፩፡፴፭–፴፯፤
፲፭፭፡፴፬–፴፡
ቅ.መ.መ. መመረጥ።
፮ *ሀ* ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ጭለማ።
፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. ጾም፣ መጾም።
ለ ቅ.መ.መ. ያህዌህ።
ሐ ቅ.መ.መ. መፍጠር፣
ፍጥረት።
መ ት. እና ቃ. ፹፯፡፡፡፣
፡፡፬–፹፪፤ ፲፲፯–፲፭።
፰ *ሀ* ት. እና ቃ. ፴፯፡፴፣
፴፱፡፲፩፤ ፴፫፡፲፤ ፲፯፤
፲፲፡፱–፲፡
ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ስጦታ።
፱ *ሀ* ሉቃ. ፭፴፡፴፱።
፲ *ሀ* ቅ.መ.መ. የነቢያት
ትምህርት ቤት።
ለ ቅ.መ.መ. ጸብ።
፲፩ *ሀ* ዮሐ. ፲፭፡፲።
ለ ፩ ዮሐ. ፪፡፲፣ ፲፭።

ነው—በአለም በሚሰሩበት ሳይሆንም፣ ቤት ይሰራ፣ በአለም አይነት ኑሮ እንድትኖሩ አልሰጠኋችሁምና፤

፲፡ ስለዚህ፣ ለዚህ ሀይል ለምትመድቡት እና ለምትሾሙት ለሶስታችሁ በማሳያችሁ ስርዓት ይሰራ።

፲፩ እና በዚህ ውስጠኛ አደባባይም፣ መጠኑ አስራ ሰባት ሜትር ስፋት ይሁን፣ እና ርዝመቱም ሀያ ሜትር ይሁን።

፲፪ እና የውስጠኛው አደባባይ የታች ክፍል ለቅዱስ ቁርባን ለማቅረብ፣ እና ለስ ብከታችሁ፣ እና ለጸማችሁ፣ እና ለጸሎታ ችሁ፣ እና ከሁሉም በላይ የሆነውን ፍላጎ ታችሁን [a]ለምታቀርቡበት ለእኔ ይቀደስ፣ ይላል ጌታ።

፲፫ እና የውስጠኛው አደባባይ ከፍተ ኛው ክፍልም ለሐዋሪያቴ ትምህርት ቤት ለእኔ ይቀደስ፣ አለ [b]አህመን ልጅ፤ ወይም በሌላ ቃላት አልፈስ፤ ወይም በሌላ ቃላት፣ አሜገስ፤ እንዲሁም [c]ጌታችሁ ኢየሱስ ክር ስቶስ። አሜን።

ክፍል ፣፲፮

በሰኔ ፩፣ ፲፰፻፱፸፫ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ ኦሀዮ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የፅዮን ከተማ ወይም ካስማ ስርዓትን በማሳየት፣ በከርትላንድ ላሉት ቅዱሳን እንደምሳሌ የተሰጠ ራዕይ። ምክንያቱ የሊቀ ካህናት ጉባኤ ነበር፣ እና የሚታሰብበት ዋናው ርዕስ ቢኖር በከርትላንድ አጠገብ ቤተክርስቲያኗ ያላትን የፍሬንች እርሻ ስፍራ የሚባለውን ምድር ስለመሸጥ ነበር። ጉባኤው ማን የእርሻ ስፍራውን በህላፊነት እንደሚወስድ መስማማት ስላልቻሉ፣ ሁሉም ጉዳዩን በመመልከት ጌታን ለመ ጠየቅ ተስማሙ።

፩ የከርትላንድ የፅዮን ካስማ ብርቱ ትሁን፤ ፪–፫ ኤጲስ ቆጶስ ውርሱን ለቅ ዱሳኑ ያካፍል፤ ፮–፱ ጆን ጆንሰን በት ብብር ስርዓት አባል ይሁን።

፩ እነሆ፣ እላችኋለሁ፣ ይህንን ጉዳይ እን ዴት ለመስራት የምታውቁበት ይህም ጥበብ ይህ ነው፣ ለፅዮን ብርታት የመሰረትኳት ይህች [a]ካስማ ጠንካራ ትሆን ዘንድ ለእኔ አስፈላጊ ነውና።

፪ ስለዚህ፣ አገልጋዬ ኒወል ኬ ውትኒ ቅዱስ ቤቴን ለመገንባት ያለምኩበትን፣ የጠቀሳችሁትን ስፍራ በህላፊነት ይው ሰድ።

፫ ደግሞም፣ በጥበብ መሰረትም፣ ውርስ ለሚፈልጉት ጥቅም ይሆን ዘንድ፣ በመካ ከላችሁ በምክር እንደሚወሰነው፣ በክፍ ልፋይ መሬቶች ይከፋፈል።

፬ ስለዚህ፣ ይህን ጉዳይ እና፣ ቃሌን ለሰዎች ልጆች ለማምጣት አላማ፣ [b]ስር ዓቴን ለመጥቀም አስፈላጊ የሆነውን ክፍል ታሚሉ ዘንድ አስታውሱ።

፭ እነሆም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ የሰ ዎች ልጆች ልብ ለእናንተ ጥቅም በቁ ጥጥር ስር ለማዋል አላማ፣ ቃሌ ወደ ሰዎች ልጆች ይሄዱ ዘንድ ይህ ለእኔ በጣም አስፈላጊ ነው። እንዲህም ይሁን። አሜን።

፮ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ይህም ጥበብ እና በእኔ አስፈላጊ ነው፣ መስዋዕቱን የተቀበልኩለት፣ እና ጸሎቱን የሰማሁለት፣ ከዚህ ጀምሮ ትእዛዛቴን እስካከበረ ድረስ

፣፲፮ [a] ሀ ት. እና ቃ. ፹፱፡ ፱–፣፲፡።
፣፲፯ [b] ሀ ት. እና ቃ. ፫፯፡ ፳።
[c] ለ ቅ.መ.መ. ጌታ።

፣፲፮ [a] ሀ ኢሳ. ፴፫፡ ፳፣ ፹፡ ፪።
ቅ.መ.መ. ካስማ።
[b] ሀ ት. እና ቃ. ፫፯፡ ፣–፡።

[c] ቅ.መ.መ. የትብብር ስርዓት።

የዘለአለም ህይወት ቃል ኪዳን የምሰጠው አገልጋዬ ጆን ጆንሰን—

፲ እርሱም ᵐየዮሴፍ ትውልድ ዘር እና ለአባቶቹ የተሰጡትን የቃል ኪዳን በረከቶች ተካፋይ ነውና—

፲፩ እውነት እላችኋለሁ፣ ቃሌን ለሰዎች ልጆች ለማምጣት ይረዳ ዘንድ እርሱ የስርዓቱ አባል መሆኑ በእኔ ዘንድ አስፈላጊ ነው።

፲፪ ስለዚህ ለዚህ በረከት ሹሙት፣ እና በዚያም ይኖርበት ዘንድ በእናንተ መካከል ከተጠቀሰው ቤት ላይ ያሉትን እዳዎች ለመውሰድ በቅንነት ይፈልግ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፯፲፯

በነሀሴ ፪፣ ፲፰፻፴፫ (እ.አ.አ.)፣ በከርትላንድ ኦሀዮ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ይህ ራዕይ፣ ነቢዩ ጌታን ለመረጃ በጠየቀበት መልስ፣ የፅዮን፣ የጃክሰን የግዛት ክፍል ሚዙሪ ቅዱሳን ጉዳዮችን የሚያመራምር ነበር። በዚህ ጊዜ በሚዙሪ የነበሩት የቤተክርስቲያኗ አባላት በጥልቅ እየተሰቃዩ ነበር እና በሐምሌ ፳፫፣ ፲፰፻፴፫ (እ.አ.አ.) ከጃክሰን የግዛት ክፍል ወጥተው እንዲሄዱ ስምምነትን እንዲፈርሙ ተገድደው ነበር።

፩–፪፣ ብዙዎቹ የፅዮን (ጃክሰን የግዛት ክፍል፣ ሚዙሪ) ቅዱሳን በእምነታቸው ተባርከዋል፤ ፫–፭፣ ፓርሊ ፒ ፕራት በፅዮን ትምህርት ቤት እንዲያገለግል ታዝዟል፤ ፮–፱፣ ቃል ኪዳናቸውን የሚያከብሩትን ጌታ ይቀበላቸዋል፤ ፣–፣፯፣ ልበ ንጹ የሆኑት እግዚአብሔርን የሚያዩበት ቤት በፅዮን ይሰራ፤ ፣፣፰–፣፣፩፣ ፅዮን ልበ ንጹህ ነች፤ ፣፣፪–፣፣፣፣ ታማኝ ከሆነች ፅዮን የጌታን ቅጣት ታመልጣለች።

፩ ባልንጀሮቼ እውነት እላችኋለሁ፣ በእውነት ትሁት ሆነው እና በቅንነት ጥበብን ለመማርና እውነትን ለማግኘት ስለሚጥሩት ብዙዎች፣ ᵐበፅዮን ምድር ስላሉት ወንድሞቻችሁ ያለኝን ፈቃድ አሳያችሁ ዘንድ በድምጼ፣ እንዲሁም በመንፈሴ ድምፅ እና ገራችኋለሁ።

፪ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ እንደ ነዚህ አይነቶች የተባረኩ ናቸው፣ ያገኙታልና፤ ፍርድንም ሳመጣባቸው ፅድቅ አደርግ ዘንድ፣ እኔ ጌታ ᵐለቅን እና ለምፈልገው ሁሉ ምህረትን አሳያለሁና።

፫ እነሆ፣ በፅዮን ስላለው ᵐትምህርት ቤት እላችኋለሁ፣ እኔ ጌታ በፅዮን ትምህርት ቤት በመኖሩ፣ ደግሞም በአገልጋዬ ᵃፓርሊ ፒ ፕራትም ተደስቻለሁ፣ እርሱም በእኔ ይኖራልና።

፬ በእኔ በመኖር የሚቀጥል ቢሆን ሌላ ትእዛዛትን እስከምሰጠው ድረስ በፅዮን ምድር ትምህርት ቤት ውስጥ በመሪነት ይቀጥላል።

፭ እናም ለትምህርት ቤቱ፣ እና ለፅዮን ውስጥ ቤተክርስቲያን መታነጽ ቅዱሳን መጻህፍትን ሁሉ እና ሚስጥራትን ለማብራራት በሚበዙ በረከቶች እባርከዋለሁ።

፮ እና ለሚቀሩት ትምህርት ቤትም፣ እኔ ጌታ፣ ምህረትን ለማሳየት ፈቃደኛ ነኝ፤ ይህም ቢሆን፣ ᵐመገሰፅ የሚያስፈልጋቸው ሌሎችም አሉ፣ እና ስራዎቻቸውም እንዲታወቁ ይደረጋል።

፣፣ᵃ ቅ.መ.መ. ዮሴፍ፣ የያዕቆብ ልጅ።
፣፣፯ ፩ᵃ ቅ.መ.መ. ፅዮን።
፪ᵃ ማቴ. ፭፡፭፤
ᵐᵃ ሞዛያ ፫፡፣፣፱።
፫ᵃ ᵐ ቅ.መ.መ. የነቢያት ትምህርት ቤት።
ᵐ ለ ቅ.መ.መ. ፕራት፣ ፓርሊ ፓርከር።
፮ᵃ ᵐ ቅ.መ.መ. መገሰጽ፣ ተግሳጽ።

፯ [ሀ]ምሳር በዛፎች ሥር ተቀምጦአል፤ እና መልካም [ለ]ፍሬ የማይሰጥ ዛፍ ሁሉ ይቈረጣል እና ወደ እሳትም ይጣላል። እኔ ጌታ ተናግሬዋለሁ።

፰ እውነት እላችኋለሁ፣ በመካከላቸው [ሀ]ልቦቻቸው [ለ]ታማኝ እንደሆኑ፣ እና እን ደተሰበሩ፣ እና መንፈሶቻቸው እንደተዋ ረዱ የሚያውቁ፣ እና ቃል ኪዳኖቻቸውን [ሐ]በመስዋዕት—አዎን፣ እኔ ጌታ በማዝዘው እያንዳንዱ መስዋእት—ለመከተል [መ]ፈቃ ደኛ የሆኑት ሁሉ፣ እኔ [ሠ]እቀበላቸዋለሁ።

፱ እኔ ጌታ በመልካም ምድር ውስጥ፣ በንጹህ ወንዝ አጠገብ እንደተተከለ፣ ውድ ፍሬዎች እንደሚሰጥ፣ በጣም ፍሬአማ እን ደሆነ ዛፍ እንዲፈሩ አደርጋለሁ።

፲ እውነት እላችኋለሁ፣ በፅዮን ምድር ውስጥ በሰጠኋችሁ [ሀ]ንድፍ መሰረት [ለ]ቤት ይሰራልኝ ዘንድ ፍቃዴ ነው።

፲፩ አዎን፣ በቶሎም በህዝቤ አስራት ይሰራ።

፲፪ እነሆ፣ ለፅዮን ደህንነት [ሀ]ቤት ለእኔ ይሰራ ዘንድ፣ ከእጆቻቸው እኔ ጌታ የምጠ ብቅባቸው [ለ]አስራትና መስዋዕት ይህ ነው—

፲፫ ለቅዱሳን ሁሉ [ሀ]ምስጋናን የማቅረ ቢያ ቦታ፣ እና በአገልግሎቱ ስራ በተለ ያዩት ጥሪአቸው እና ሀላፊነታቸው የተጠ ሩት ሁሉ የሚማሩበት ቦታ፤

፲፬ በአገልግሎታቸው፣ በአስተያየታ ቸው፣ በመሰረታዊ መርህ፣ እና በትምህ ርታቸው፣ እና በላያችሁ የተሰጣችሁ የመ ንግስቱ [ሀ]ቁልፍ፣ በምድር ላይ ያለው የእግ ዚአብሔር [ለ]መንግስትን በሚመለከት ሁሉ፣ በዚህ ሁሉ ፍጹም [ሐ]መረዳት ይኖራቸው ዘንድ ነው።

፲፭ እና በጌታ ስም ቤትን ለእኔ እስከሰሩ ልኝ ድረስ፣ እና እንዳይረከስ፣ ማንኛው ንም [ሀ]እርኩስ ነገር እንዲገባበት እስካልፈ ቀዱ ድረስ፣ [ለ]ክብሬ ያርፍበታል፤

፲፮ አዎን፣ እና በዚያም [ሀ]እገኛለሁ፣ እመጣበታለሁና፣ እና የሚገባበት [ለ]ንጹህ ልብ ያለው ሁሉ እግዚአብሔርን ያያል።

፲፯ ነገር ግን የረከሰ ቢሆን አልመጣበ ትም፣ እና ክብሬም አይገኝበትም፤ ቅዱስ ወዳልሆነ ቤተመቅደስ አልመጣምና።

፲፰ እሁንም እነሆ፣ ፅዮን እነዚህን ነገሮች ካደረገች [ሀ]ትበለፅጋለች፣ እና ታድጋለችም እናም በጣም የከበረች፣ በጣም ታላቅ፣ እና በጣም አስፈሪም ትሆናለች።

፲፱ እና የምድር [ሀ]ህዝብም ያከብሯታል፣ እና እንዲህም ይላሉ፥ በእርግጥም [ለ]ፅዮን የእግዚአብሔር ከተማ ነች፣ እና በእርግ ጥም ፅዮን ልትወድቅ አትችልም፣ ወይም ከስፍራዋ አትወጣም፣ እግዚአብሔር በዚያ ነውና፣ እና የጌታም እጅ በዚያ ነው፤

፳ እና በጉልበቱ ሀይል መድህኒቷና ታላቅ [ሀ]ማማዋ እንደሚሆን መሀላ ገብቷል።

፳፩ ስለዚህ፣ በእውነት ጌታ እንዲህ ይላል፣ [ሀ]ፅዮን ትደሰት፣ ይህች ፅዮን ነውና—ልበ ንጹህ፤ ስለዚህ፣ ኃጥአን ሁሉ ሲያዝኑ ፅዮን ትደሰት።

፯ ሀ ማቴ. ፫፥፲።
ለ ሉቃ. ፮፥፵፫–፵፭፤
አልማ ፭፥፴፮፤ ፶፪፤
፫ ኔፊ ፲፬፥፲፭–፳።
፰ ሀ ቅ.መ.መ. የተሰበረ ልብ።
ለ ቅ.መ.መ. ታማኝ፣
ታማኝነት።
ሐ ቅ.መ.መ. መስዋዕት።
መ ት. እና ቃ. ፰፬፥፴፬።
ሠ ት. እና ቃ. ፶፪፥፲፭፤
፻፴፪፥፶።
፲ ሀ ት. እና ቃ. ፻፲፭፥፲፬–፲፮።
ለ ት. እና ቃ. ፶፯፥፫፤
፹፰፥፻፲፱፤ ፻፳፬፥፶፩።
፲፪ ሀ ቅ.መ.መ. ቤተመቅደስ፣
የጌታ ቤት።
ለ ቅ.መ.መ. አስራት፣
አስራት መክፈል።
፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. አመስጋኝ፣
ምስጋናን፣ ምስጋና
መስጠት።
፲፬ ሀ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር
መንግስት ወይም
መንግስተ ሰማያት።
ለ ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
ሐ ቅ.መ.መ. ማስተዋል።
፲፭ ሀ ት. እና ቃ. ፺፬፥፱፤
፻፱፥፳–፳፩።
ለ ሐጌ. ፪፥፯፤
ት. እና ቃ. ፹፬፥፭።
፲፮ ሀ ት. እና ቃ. ፻፲፥፩–፲።
ለ ማቴ. ፭፥፰፤
ት. እና ቃ. ፰፯፥፲–፲፫፤
፹፰፥፰፰።
ቅ.መ.መ. ንጹህ፣ ንጹህነት።
፲፰ ሀ ት. እና ቃ. ፺፥፳፬፤ ፻፥፲፭።
፲፱ ሀ ኢሳ. ፰፥፲፬፤
ዘካ. ፪፥፲–፲፪፤
ት. እና ቃ. ፵፭፥፰፮–፸፩፤
፵፱፥፲።
ለ ቅ.መ.መ. አዲሲቱ
ኢየሩሳሌም።
፳ ሀ ፪ ሳሙ. ፳፪፥፫።
፳፩ ሀ ሙሴ ፯፥፲፰።
ቅ.መ.መ. ንጹህ፣ ንጹህነት፤
ፅዮን።

፳፪ እነሆም፣ እና አስተውሉ፣ በኃጢአተ ኞቹ ላይ ᵐበቀል እንደ አውሎ ንፋስ ፈጥኖ መጥቷል፤ እና ማንስ ያመልጠዋል?

፳፫ የጌታ ᵐመከራም ቀንና ሌሊት ያል ፋል፤ ወሬውንም መላውን ህዝብ ያስደነ ግጣል፤ አዎን፣ ጌታ እስከሚመጣም አይ ቆምም፤

፳፬ የጌታ ቁጣ በርኩሰታቸውና በክፉ ስራዎቻቸው ሁሉ ላይ ተቀጣጥሏልና።

፳፭ ይህም ቢሆን፣ ፅዮን ያዘዝኳትን ማን ኛውም ነገሮች ሁሉ የምትከተል ከሆነችም ᵐታመልጣለች።

፳፮ ነገር ግን፣ ያዘዝኳትን ማንኛውም ነገ ሮች ሁሉ ባትከተል ግን፣ በሁሉም ስራዎቿ መሰረት በታላቅ ስቃይ፣ ᵐቸነፈር፣ መቅ ሰፍት፣ በጎራዴ፣ ᵃበበቀል፣ ᵇበምትበላም እሳት ᶜእነበኛታለሁ።

፳፯ ይህም ቢሆን፣ እኔ ጌታ መስዋዕቴን እንደተቀበልኩ በጆሮዋ ይህ አንድ ጊዜ ይነ በብላት፤ እና ኃጢአት ከዚህ በኋላ የማ ትሰራ ቢሆን ከእነዚህ ነገሮች ᵐማንኛቸውም አይደርሱባትም።

፳፰ እና በበረከቶች ᵐእባርካታለሁ፣ እና በእርሷና በትውልዶቿ ላይ ለዘለአለም የሚ ሆኑ በረከቶች አበዛላታለሁ፣ ይላል ጌታ አምላካችሁ። አሜን።

ክፍል ፯፰

በነሀሴ ፯፣ ፲፰፻፱ (እ.አ.አ.)፣ በኪርትላንድ ኦሀዮ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ይህ ራዕይ የመጣው በሚዙሪ ቅዱሳን በመሰደዳቸው ምክንያት ነበር። ተጨማሪ የቤተክርስቲያኗ አባላት በምዙሪ መስፈራቸው፣ በቅዱሳን ቁጥ ሮች፣ በፖለቲካና በኢኮኖሚ ተፅዕኖአቸው፣ እና በባህልና በሀይማኖት ልዩነቶች ምክንያት ፍርሀት የነበራቸውን አንዳንድ ሌሎች ሰፋሪዎችን ረብሾ ነበር። በሀምሌ ፲፰፻፱ (እ.አ.አ.)፣ አመጸኛ ህዝብ የቤተክርስቲያኗን ንብረት አፈረሱ፣ ሁለት የቤተክርስቲያኗ አባላትን ሬንጅ ቀብተው በላባ ሸፈኑ፣ እናም ቅዱሳን ከጃክሰን አውራጃ ወጥተው እንዲሄዱ በግድ ጠየቁ። ምንም እንኳ በሚዙሪ የነበሩት ችግ ሮች ዜና ለነቢዩ በኪርትላንድ ውስጥ (በዘጠኝ መቶ ማይል ርቀት) እንደደረሰው ምንም ጥርጣሬ ባይኖርም፣ የጉዳዩ አሳሳቢነት በዚህ ቀን ሊታወቀው የሚችለው በራዕይ ብቻ ነበር።

፩–፫፣ የቅዱሳኑ ስቃይ ለጥቅማቸው ይሆ ናል፤ ፬–፰፣ ቅዱሳን ለሀገሩ ህገ መንግ ስት ተባባሪዎች ይሁኑ፤ ፱–፲፣ ታማኝ፣ ብልህ፣ እና መልካም ሰዎች በህዝባዊ መንግስት መደገፍ ይገባቸዋል፤ ፲፩–፲፭፣ በጌታ ምክንያት ህይወታቸውን የሚ ያጡ ዘለአለማዊ ህይወት ይኖራቸዋል፤ ፲፮–፲፰፣ ጦርነትን አስወግዱ እና ሰላምን አውጁ፤ ፲፱–፳፪፣ የኮርትላንድ ቅዱሳን ተገሰጹ እናም ንስሀ እንዲገቡ ታዘዙ፤ ፳፫–፳፱፣ ጌታ በህዝቦቹ ላይ የተጣለባ ቸውን ስቃይ እና መከራን የሚያስተዳ ድሩ ህጎቹን ጌታ ገለጠ፤ ፴፫–፴፰፣ ጦር ነት ተቀባይነት የሚያገኘው ጌታ ሲያ ዝዘው ነው፤ ፴፱–፴፭፣ ቅዱሳን፣ ንስሀ ቢገቡ የጌታን በቀል ለማምለጥ ለሚችሉ ጠላቶቻቸውን ይቅርታን ይስጡ።

፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. በቀል።
፳፫ ሀ ኢሳ. ፳፰፡ ፲፡–፲፱፤
ት. እና ቃ. ፴፮፡ ፴፩።
፳፭ ሀ ፪ ኔፊ ፮፡ ፲፫–፲፰፤
ት. እና ቃ. ፳፫፡ ፴፡፡
ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፡ ፳።
፳፯ ሀ ሉቃ. ፳፩፡ ፲–፲፫።
ለ ሚል. ፡፡ ፩–፫፤
፫ ኔፊ ፳፩፡ ፳–፳፩።
ሐ ኢዩ. ፩፡ ፲፭–፳።
መ ት. እና ቃ. ፹፡፡ ፹–፹፩።
፳፯ ሀ ሕዝ. ፲፰፡ ፳፯።
፳፰ ሀ ቅ.መ.መ. መባረክ፣
የተባረከ፣ በረከት።

፩ ባልንጀሮቼ እውነት እላችኋለሁ፣ ᵐአትፍሩ፣ ልባችሁ ይፅኑ፤ አዎን፣ ዘወ ትር ተደሰቱ፣ እና በሁሉም ነገሮች ᵃምስ ጋናን ስጡ፤

፪ ጌታን በትዕግስት ᵐጠብቁ፣ ጸሎቶቻ ችሁ ወደፀባአት ጌታ ጆሮዎች ገብተዋል፣ እናም በዚህ ህትመት እና ምስክር ተመዝግ በዋልና—እነዚህም እንዲፈጸሙ ጌታ መሀላ ገብቷል እና አውጇል።

፫ ስለዚህ፣ እንዲሟሉም በማይለወጥ ቃል ኪዳን፣ ይህን የተሰፋ ቃል ይሰጣችኋል፤ እና ᵐየተሰቃያችሁባቸው ነገሮች ሁሉ ለጥ ቅማችሁ፣ እና ለክብሬ፣ አብረው ይሰራሉ፣ ይላል ጌታ።

፬ አሁንም፣ ስለምድሩ ህግጋት በእው ነትም እላችኋለሁ፣ ህዝቤ የማዝዛቸውን ማንኛቸውንም ነገሮች ሁሉ እንዲያደርጉ ፍቃዴ ነው።

፭ እና መብቶችን እና ልዩ መብቶችን በመጠበቅ የነጻነትን መሰረታዊ መርህ የሚ ደግፈው፣ ᵐህገ መንግስት የሆነው የምድሩ ᵃህግ ለሰው ዘር ሁሉ ነው፣ እና በፊቴም ተገቢ ነው።

፮ ስለዚህ፣ እኔ ጌታ እናንተና የቤተክርስ ቲያኔ ወንድሞቻችሁ ለዚያ ለሀገሩ ህገ መን ግስት ተባባሪዎች መሆናችሁን ተገቢ አደ ርጋችኋለሁ፤

፯ የሰው ህግን በሚመለከትም፣ ከዚህ በላይ ወይም በታች የሆነው ከክፉ የሚ መጣ ነው።

፰ እኔ ጌታ አምላክ ነጻ አደረኳችሁ፣ ስለ ዚህ በእርግጥም ᵐነጻ ናችሁ፤ እና ህጉም ነጻ አድርጎአችኋል።

፱ ይህም ቢሆን፣ ᵐክፉው ሲያስተዳድር ህዝቡ ያዝናል።

፲ ስለዚህ፣ ᵐታማኝ ሰዎች እና ብልህ ሰዎች በቅንነት ይፈለጉ፣ እና መልካምና ብልህ ሰዎች ለመደገፍ ፈልጉ፤ አለበለዚ ያም ከዚህ በታች የሆኑት ማንኛውም ከክፉ የመጣ ነው።

፲፩ እና ከእግዚአብሔር አንደበት ከሚ መጣው በእያንዳንዱ ᵐቃል እንድትኖሩ ዘንድ፣ ክፉን ሁሉ እንድትተዉና በጥሩ ነገ ሮች ላይ እንድትጸኑ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ።

፲፪ ታማኝ ለሆነው በሥርዓት ላይ ሥር ዓት፣ በትእዛዝም ላይ ትእዛዝ ᵐእሰጠዋለ ሁና፤ እና በዚህም ᵃእሞክራችኋለሁ እናም እፈትናችኋለሁም።

፲፫ እና ለእኔ ጉዳይ፣ ለስሜ ህይወቱን ᵐየሚሰጥም ዳግም ያገኘዋል፣ እንዲሁም ዘለአለማዊ ህይወትን።

፲፬ ስለዚህ፣ ጠላቶቻችሁን ᵐአትፍሩ፣ በቃል ኪዳኔ፣ ᵃእስከሞትም ድረስ፣ እን ደምትጸኑ፣ ብቁም ሆናችሁ እንድትገኙ፣ በሁሉም ነገሮች ᶜእፈትናችሁ ዘንድ በልቤ አውጄዋለሁና፣ ይላል ጌታ።

፲፭ በቃል ኪዳኔ ካልጸናችሁ ለእኔ ብቁ አይደላችሁም።

፲፮ ስለዚህ፣ ᵐጦርነትን ᵃአስወግዱና ᶜሰላምንም አውጁ፣ እና የልጆችን ልብ ወደ አባቶች፣ እና የአባቶችንም ልብ ወደ ልጆች ᵐለመቀየር በቅንነት ፈልጉ፤

፯፰ ፩ *ሀ* ት. እና ቃ. ፰፰፡ ፭።
ለ ቅ.መ.መ. አመስጋኝ፣ ምስጋናን፣ ምስጋና መስጠት።
፪ *ሀ* መዝ. ፰፭፡ ፲፩፤ ኢሳ. ፴፡ ፲፰–፲፱፤ ት. እና ቃ. ፻፴፫፡ ፴፭።
፫ *ሀ* ት. እና ቃ. ፻፰፡ ፯።
ቅ.መ.መ. ጭንቀት።
፭ *ሀ* ት. እና ቃ. ፻፩፡ ፫፯–፴፣ ፻፱፡ ፻፴።
ቅ.መ.መ. ህገ መንግስት፤ መብት።
ለ ፩ ጴጥ. ፪፡ ፲፣–፲፩፤ ት. እና ቃ. ፻፰፡ ፴፭–፴፰፤ ፻፴፬፡ ፭።
፭ *ሀ* ዮሐ. ፰፡ ፴፪፤ ፪ ቆሮ. ፣፡ ፲፯።
ቅ.መ.መ. ነጻ ምርጫ፤ ነጻ፣ ነጻነት።
፱ *ሀ* ምሳ. ፳፱፡ ፪።
፲ *ሀ* ቅ.መ.መ. ታማኝ፣ ታማኝነት።
፲፩ *ሀ* ዘዳግ. ፰፡ ፣፤ ማቴ. ፬፡ ፬፤ ት. እና ቃ. ፹፬፡ ፴፣–፴፬።
፲፪ *ሀ* ኢሳ. ፳፰፡ ፲፣ ት. እና ቃ. ፴፪፡ ፰፰፤
ለ አብር. ፣፡ ፳፭–፳፯።
፲፣ *ሀ* ሉቃ. ፱፡ ፳፬፤ ት. እና ቃ. ፻፩፡ ፴፭–፴፰፤ ፻፣፡ ፳፯–፳፰፡ ፴፡ ፴፱፤ ቅ.መ.መ. ሰማዕት፣ ሰማዕትነት።
፲፬ *ሀ* ነህ. ፬፡ ፲፬፤ ት. እና ቃ. ፻፳፪፡ ፱።
ለ ራዕ. ፪፡ ፣፤ ት. እና ቃ. ፻፴፯፡ ፴፩፣ ፴፱።
ሐ ት. እና ቃ. ፻፳፬፡ ፻፭።
፲፭ *ሀ* ቅ.መ.መ. ጦርነት።
ለ አልማ ፴፰፡ ፲፬።
ቅ.መ.መ. ሰላም የሚሰራ።
ሐ ቅ.መ.መ. ሰላም።
መ ሚል. ፬፡ ፭–፮፤ ት. እና ቃ. ፪፡ ፩–፪።

፲፯ ደግሞም፣ Ꮎየአይሁዶችን ልብ ወደ ነቢያት፣ እና የነቢያትንም ወደ አይሁዶች፤ አለበለዚያም እመጣና አለምን ሁሉ በእር ግማን እመታታለሁ፣ እና በፊቴ ስጋ ለባሽ ሁሉ ይቃጠላል።

፲፰ ልባችሁ አይታወኩ፤ በአባቴ ቤት Ꮎብዙ መኖሪያዎች አሉ፤ እና ስፍራን አዘ ጋጅቼላችኋለሁና፤ እናም አባቴ እና እኔ ባለንበት እናንተም ደግሞ ትሆናላችሁ።

፲፱ እነሆ፣ እኔ ጌታ በከርትላንድ ቤተክ ርስቲያን ውስጥ ባሉት ብዙዎች አልተደ ሰትኩም፤

፳ ኃጢአታቸውን፣ እና ክፉ መንገዶቻ ቸውን፣ የልባቸውን ኩራት፣ እና መጎምጀ ታችን፣ እና ርኵሰታቸውን አይተውም፣ እና የሰጠኋቸውን የጥበብ እና የዘለአለም ቃላትን አይከተሉም።

፳፩ እውነት እላችኋለሁ፣ ንስሀ ባይገቡ እና ያልኳቸውን ማንኛቸውንም ነገሮች ባታደርጉ፣ እኔ ጌታ Ꮎእገስጻቸዋለሁ እና የፈቀድኩትን ሁሉ አደርጋለሁ።

፳፪ ደግሜም እላችኋለሁ፣ ያዘዝኳችሁን ማንኛቸውንም ነገሮች Ꮎብታደርጉ፣ እኔ ጌታ ቁጣን እና ንዴትን ከእናንተ አርቃለሁ፣ እና የሲያል ᏽደጆችም አያሸንፏችሁም።

፳፫ አሁን፣ ስለቤተሰቦቻችሁ በሚመ ለከት እናገራችኋለሁ—ሰዎች እናንተን ወይም ቤተሰቦቻችሁን አንዴ Ꮎቢመቷ ችሁ፣ እና በትዕግስት ብትጸኑ እና እነር ሱንም ባትሰድቡ ወይም በቀልንም ባታደ ርጉ፣ ዋጋን ታገኛላችሁ፤

፳፬ ነገር ግን በትዕግስት ባትጸኑ፣ በእና ንተ ላይ Ꮎእንደተመዘነ ትክክለኛ ሚዛን ሆኖ ይቆጠራል።

፳፭ ደግሞም፣ ጠላታችሁ ለሁለተኛ ቢመታችሁ፣ እና ጠላታችሁን ባትሰድቡ፣ እና በትዕግስት ብትጸኑ፣ ዋጋችሁ አንድ መቶ እጥፍ ይሆናል።

፳፮ ደግሞም፣ ለሶስተኛ ጊዜ ቢመታ ችሁ፣ እና Ꮎበትዕግስትም ብትጸኑ፣ ዋጋ ችሁ በአራት እጥፍ ያድጋል፤

፳፯ እና እነዚህ ሶስት ምስክሮችም ንስሀ ባይገባ በጠላታችሁ ላይ ይቆማሉ፣ እናም አይወገዱም።

፳፰ አሁንም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ያ ጠላት ወደ ፍርድ በፊቴ ባለመምጣቱ ከበቀሌ ካመለጠ፣ ዳግም ወደ እናንት ወይም ወደ ቤተሰባችሁ፣ እንዲሁም እስከ ሶስት እና አራት ትውልዶች ልጅ ልጆቻ ችሁ እንዳይመጣባችሁ በስሜ Ꮎአስጠንቅ ቁት።

፳፱ ከዚያም፣ በእናንተ ወይም በልጆቻ ችሁ፣ ወይም እስከ ሶስትና አራት ትው ልዶች በልጅ ልጆቻችሁ ከመጣባችሁ፣ ጠላታችሁን በእጆቻችሁ አሳልፌ እሰጣ ችኋለሁ።

፴ ከዚያም ካልቀጣችሁት፣ እናንት ደግ ሞም ልጆቻችሁ እና እስከ ሶስት እና አራት ትውልዶች የልጅ ልጆቻሁም ለፅድቃችሁ ዋጋን ታገኛላችሁ።

፴፩ ይህም ቢሆን፣ ጠላታችሁ በእጆቻ ችሁ ውስጥ ነው፤ እና በስራው በኩል ዋጋ ከሰጣችሁት ተገቢን ነገር አደረጋችሁ፤ ህይወታችሁን የሚሻ ቢሆን፣ እና ህይወ ታችሁ በእርሱ አደጋ ላይ ከሆነ፣ ጠላታ ችሁ በእጆቻችሁ ውስጥ ነው እና ተገቢ ንም ነገር አደረጋችሁ።

፴፪ እነሆ፣ ይህም ለአገልጋዬ ኔፊ፣ እና Ꮎለአባቶቻችሁ፣ ለዮሴፍ፣ እና ያዕቆብ፣ እና ለይስሀቅ፣ እና ለአብርሐም፣ እና ለቀ ደሙት ነብያቴ እና ሐዋሪያቴ የሰጠሁት ህግ ነው።

፲፯ Ꮎ ቅ.መ.መ. አይሁዶች።
፲፰ Ꮎ ዮሐ. ፲፬፡፪፣
ት. እና ቃ. ፶፱፡፪፣
ሮሜ፡ ፲፲፭፣ ፹፬፡፯።
፳፩ Ꮎ ሞዛያ ፳፫፡፳፩፣
ሔለ. ፲፪፡፫።
ቅ.መ.መ. መገሰጽ፣ ተግሳጽ።
፳፪ Ꮎ ቅ.መ.መ. ታዛዥነት፣
ታዛዥ፣ መታዘዝ።
ለ ማቴ. ፲፯፡፲–፲፰፣
ት. እና ቃ. ፴፫፡፲–፲፫።
፳፫ Ꮎ ሉቃ. ፮፡፳፱፣
አልማ ፴፫፡፴፯–፴፰።
ቅ.መ.መ. ማሳደድ፣
መሳደድ።
፳፬ Ꮎ ማቴ. ፯፡፩–፪።
፳፭ Ꮎ ቅ.መ.መ. ትዕግስት።
፳፮ Ꮎ ቅ.መ.መ. ማስጠንቀቅ፣
ማስጠንቀቂያ።
፴፪ Ꮎ ት. እና ቃ. ፳፯፡፲።

፴፫ ደግሞም፣ ከየትኞቹም ሀገሮች፣ ነገ
ዶች፣ ቋንቋዎችና ህዝብ ጋር እኔ ጌታ ካላ
ዘዝኳቸው በስተቀር እንዳይዋጉ ለጥንቶቹ
የሰጠሁት ᐟህግ ነው።

፴፬ እና የትኛውም ሀገር፣ ነገድ፣ ወይም
ህዝብ በእነርሱ ላይ ጦርነት ቢያውጅ፣
እነርሱ አስቀድመው ለዚያ ህዝብ፣ ሀገር፣
ወይም ቋንቋ ᐟየሰላም አርማን ያንሱ፤

፴፭ እና ህዝቦቹ ለሰላም ያቀረቡትን፣
ወይም ሁለተኛውን ወይም ሶስተኛውን፣
ባይቀበሉ፣ እነዚህን ምስክሮች በጌታ ፊት
ያምጡ፤

፴፮ ከዚያም እኔ ጌታ ትእዛዝን እሰጣቸ
ዋለሁ፣ እና ከእነዚያ ሀገሮች፣ ቋንቋዎችና
ህዝብ ጋር ጦርነትን ቢያደርጉ ድርጊታቸ
ውን ተገቢ ብዬ እቀበለዋለሁ።

፴፯ እና እኔ ጌታ ጦርነታቸውን፣ እና
እስከ ሶስት እና አራት ትውልድ፣ የልጆ
ቻቸውን ጦርነት፣ እና የልጅ ልጆቻቸውን
ጦርነት፣ በጠላቶቻቸውም ላይ በቀልን እስ
ኪያገኙ ድረስ ᐟእዋጋላቸዋለሁ።

፴፰ እነሆ፣ ይህም በፊቴ ተገቢ ይሆን
ዘንድ ለሁሉም ህዝብ ምሳሌ ነው፣ ይላል
ጌታ አምላካችሁ።

፴፱ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣
ለመጀመሪያ ጊዜ ጠላታችሁ ወደ እናንተ
ከመጣ በኋላ ንስሀ ቢገባ እና ለምህረት ወደ
እናንተ እየለመነ ቢመጣ፣ ይቅርታ አድር
ጉለት፣ እና በጠላታችሁም ላይ እንደምስ
ክር አትያዙበት—

፴ እናም እስከ ሁለተኛና ሶስተኛ ድረስም
ይቀጥል፤ እና ጠላታችሁ በእናንተ ላይ የተ
ላለፈውን ንስሀ እስከገባለት ድረስ፣ እናንት
እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት ᐟይቅር በሉት።

፴፩ እና በመጀመሪያው ከተላለፋችሁ
እና ንስሀ ካልገባ፣ ይህም ቢሆን ይቅርታ
ስጡት።

፴፪ እና ለሁለተኛ ጊዜ ከተላለፋችሁ፣
እና ንስሀን ባይገባ፣ ይህም ቢሆን ይቅር
ታን ስጡት።

፴፫ እና ለሶስተኛ ጊዜ ቢተላለፋችሁ፣ እና
ንስሀን ባይገባ፣ ደግሞም ይቅርታን ስጡት።

፴፬ ነገር ግን ለአራተኛ ጊዜ ቢተላለፋ
ችሁ ይቅርታ አትስጡት፣ ነገር ግን እነዚ
ህን ምስክሮች በጌታ ፊት አምጡ፤ እና ንስሀ
እስከሚገባ ድረስ እና በእናንተ ላይ በተላለ
ፈው ነገሮች ሁሉ በአራት እጥፍ ዋጋ እስከ
ሚሰጣችሁ ድረስ አይደመሰሱም።

፴፭ ይህን ቢያደርግ፣ በሙሉ ልባችሁ
ይቅርታን ትሰጡታላችሁ፤ እና ይህን ባያ
ደርግ፣ እኔ ጌታ በጠላታችሁ ላይ በአንድ
መቶ እጥፍ ᐟእበቀላለሁ፤

፴፮ እናም በሚጠሉኝ በልጆቹ ላይ፣ እና
በልጅ ልጆቹ ላይ ሁሉ፣ እስከ ᐟሶስትና
አራት ትውልድ እበቀላለሁ።

፴፯ ነገር ግን፣ ልጆቹ ወይም የልጅ
ልጆች ንስሀ ቢገቡ፣ እና በሙሉ ልባቸው
እና በሙሉ ሀይላቸው፣ አዕምሮዋቸው፣
እናም ጉልበታቸው ወደ ጌታ ᐟቢመለሱ፣
እና ለተላለፉት መተላለፊያዎች፣ ወይም
አባቶቻቸው፣ ወይም የአባቶቻቸው አባ
ቶች ለተላለፉበት ሁሉ በአራት እጥፍ ደግ
መው ቢመለሱ፣ ከዚያም የእናንተም ቁጣ
ይመለስ፤

፴፰ እና ᐟበቀልም አይመጣባቸውም፣
ይላል ጌታ አምላካችሁ፣ እና መተላለፉ
ቸውም በጌታ ፊት እንደ ምስክር በእነርሱ
ላይ አይመጡባቸውም። አሜን።

ክፍል ፲፬

በነሀሴ ፳፬፣ ፲፰፻፲፭ (እ.አ.አ.) በሀይረም ኦሀዮ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል

፴፫ ᐟ ዘዳግ. ፳፡ ፲፣
አልማ ፴፰፡ ፲፬–፲፮።
፴፬ ᐟ ት. እና ቃ. ፲፭፡ ፴፰–፴፭።
፴፭ ᐟ ኢያ. ፳፫፡ ፲፣
ኢሳ. ፴፱፡ ፳፭።
፴ ᐟ ማቴ. ፲፰፡ ፳፩–፳፪፣
ት. እና ቃ. ፳፬፡ ፱–፲፩።
ቅ.መ.መ. ይቅርታ ማድረግ።
፴፩ ᐟ ሞር. ፰፡ ፳።
፴፪ ᐟ ዘዳግ. ፭፡ ፱–፲።
፴፫ ᐟ ሞዛያ ፤፡ ፴፫፣ ሞር. ፱፡ ፤።
፴፬ ᐟ ሕዝ. ፲፰፡ ፲፱–፳፫።

ለጆን መርዶክ የተሰጠ ራዕይ። ባለቤቱ ጁሊያ ክላፕ በሚያዝያ ፲፰፻፸፭ (እ.አ.አ.) ከሞተች በኋላ፣ እናት የሌላቸው ልጆቹ ከሌሎች ቤተሰቦች ጋር እየኖሩ ሳሉ፣ ከአንድ አመት በላይ፣ ጆን መርዶክ ወንጌልን ይሰብክ ነበር።

፩–፰፣ ጆን መርዶክ ወንጌልን እንዲሰብክ ተጠራ፣ እና እርሱን የሚቀበሉትም ጌታን ይቀበላሉ እና ምህረትንም ያገኛሉ።

፩ እነሆ፣ ለአገልጋዬ ጆን መርዶክ ጌታ እንዲህ ይላል—ወደ ምስራቅ ሀገሮች ከቤት ወደ ቤት፣ ከመንደር ወደ መንደር፣ እና ከከተማ ወደ ከተማ ዘለአለማዊ ወንጌሌን በዚያ ለሚኖሩት፣ [ሀ]በስደት እና በክፋት መካከል እያወጅህ እንድትሄድ ተጠር ተሀል።

፪ እና [ለ]የሚቀበልህም ይቀበለኛል፤ እና በእኔ ቅዱስ መንፈስ [ሐ]መገለጥ ቃሌን ለማ ወጅ ሀይል ይኖርሀል።

፫ እናማንም [መ]እንደ ትንሽ ልጅ የሚቀበ ልህም፣ [ሠ]መንግስቴን ይቀበላል፤ እነርሱም ብፁዓን ናቸው፥ [ረ]ምህረት ያገኛሉና።

፬ እና ማንም አንተን [ሰ]የሚቃወም ከአባቴ እና ከቤቴ ይወገዳል፤ እና በእግረ መንገድህ በእነርሱም ላይ ምስክር ይሆን ዘንድ በተ ሰወሩ ስፍራዎች [ቀ]እግሮችህን ታጸዳለህ።

፭ እነሆ እና አስተውል፣ በመጽሐፍም ጥራዝ እንደ ተጻፈው፣ በእኔ ላይ ከፅድቅ በመራቅ ክፉ ሥራቸው ሁሉ እወቀሳቸው ዘንድ፣ [በ]ለፍርድ በቶሎ [ተ]እመጣለሁ።

፮ አሁንም፣ እውነት እልሀለሁ፣ ልጆች ህን እስክታስተዳድር እና በመልካም ወደ ፅዮን ኤጲስ ቆጶስ እስኪላኩ ድረስ እንድ ትሄድ ፍቃዴ አይደለም።

፯ እና ከጥቂት አመታት በኋላ፣ በእኔ የም ትሻ ከሆነ፣ ውርስህን ለመቀበል ወደ መል ካሚቱ ምድር መሄድ ትችላለህ፤

፰ አለበለዚያ እስከምትወሰድ [ተ]ድረስ ወን ጌሌን በማወጅ ትቀጥላለህ። አሜን።

ክፍል ፲

በጥቅምት ፲፪፣ ፲፰፻፸፭ (እ.አ.አ.) በፔሪስበርግ ኒው ዮርክ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ እና ለስድኒ ሪግደን የተሰጠ ራዕይ። ሁለቱ ወንድሞች፣ ለብዙ ቀናት ከቤተሰቦ ቻቸው ተለያይተው ስለነበር፣ ስለእነርሱ አስበው ነበር።

፩–፬፣ ጆሴፍ እና ስድኒ ለነፍሳት ደህን ነት ወንጌሉን ይስበኩ፤ ፭–፰፣ የሚናገ ሩትም በዚያች ሰዓት ይሰጣቸዋል፤ ፱–፲፪፣ ስድኒ ቃል ተቀባይ ይሁን እና ጆሴፍ ገላጭ እና በምስክርም ሀያል ይሁን፤ ፲፫–፲፯፣ ጌታ ንጹህ ህዝብ ያነሳል፣ እና የሚ ታዘዙም ይድናሉ።

፩ በእውነት ባልንጀሮቼ [ሀ]ስድኒ እና [ለ]ጆሴፍ፣ ጌታ ለእናንተ እንዲህ ይላል፣ ቤተሰቦቻችሁ ደህና ናቸው፤ በእጆቼም ውስጥ ናቸው፣ እና መልካም እንደሚ መስለኝም አደርግባቸዋለሁ በእኔ ሁሉም ሀይል አለና።

፪ ስለዚህ፣ ተከተሉኝ፣ እና የምሰጣችሁ ንም ምክር አድምጡ።

፯፡፡ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. ማሳደድ፣ መሳደድ።
፪ ሀ ማቴ. ፲፡ ፴፯።
ለ ፩ ቆሮ. ፪፡ ፱–፭።
፫ ሀ ማቴ. ፲፰፡ ፩–፭።
ለ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር መንግስት ወይም መንግስተ ሰማያት።
ሐ ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።
፬ ሀ ዮሐ. ፲፪፡ ፵፬–፵፡
ለ ት.እና ቃ. ፴፡ ፴–፴፪።
፭ ሀ ይሁዳ ፩፡ ፲፡–፲፭።
ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—ዳኛ።
ለ ት.እና ቃ. ፩፡ ፲፩–፲፡
፰ ሀ ማቴ. ፲፡ ፲፡ ፳፪፡
፲ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. ሪግደን፣ ስድኒ።
ለ ቅ.መ.መ. ስሚዝ፣ ጆሴፍ ዳግማዊ።

፫ እነሆ፣ እናም አስተውሉ፣ በዚህ ስፍራ፣ በዚህ ክፍለ ሀገር አካባቢ ብዙ ህዝብ አሉኝ፤ እና ውጤታማ በር በዚህ አካባቢ፣ በዚህ በምስራቅ ምድር ውስጥ ይከፈታል።

፬ ስለዚህ፣ እኔ ጌታ ወደዚህ ስፍራ ትመጡ ዘንድ ፈቀድኩኝ፤ ለነፍሳትም [ሀ]ደህንነት ይህም በእኔ ዘንድ አስፈላጊ ነበርና።

፭ ስለዚህ፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ወደ እነዚህ ህዝብ ድምጾቻችሁን ከፍ አድርጉ፤ በልባችሁ የምጨምረውን ሀሳብ [ሁ]ተናገሩ፣ እና በሰዎችም ፊት አታፍሩም፤

፮ የምትናገሩት በዚያች ሰዓት፣ አዎን፣ በዚያች ጊዜም፣ ምን እንደምትናገሩ [ሂ]ይሰጣችኋልና።

፯ ነገር ግን የምታውጁትን ማንኛውንም ነገር በስሜ፣ በሁሉም ነገሮች በተረጋጋ ልብ፣ [ሃ]በትሁት መንፈስ [ሄ]ታውጁ ዘንድ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ።

፰ እና ይህን የተስፋ ቃል እሰጣችኋለሁ፣ ይህን ስታደርጉ ለምትሉት ማንኛቸውም ነገሮች ሁሉ ምስክር ይሰጣችሁ ዘንድ [ሆ]መን ፈስ ቅዱስ ይላካል።

፱ እና አንተ አገልጋዬ ስድኒ ለዚህ ህዝብ [ሀ]ቃል ተቀባይ እንድትሆን ፍቃዴ ነው፤ አዎን፣ በእውነትም በዚህ ሀላፊነት፣ እን ዲሁም እንደ አገልጋዬ ጆሴፍ ቃል ተቀባይ እንድትሆኑ፣ እሾምሀለሁ።

፲ እና ለእርሱም [ለ]በምስክር ሀያል እንዲ ሆን ሀይል እሰጠዋለሁ።

፲፩ እና ቅዱሳን መጻህፍትን ሁሉ ለመዘ ርዘር [ሐ]ሀያል እንድትሆንም ዘንድ፣ ለእር ሱም ቃል ተቀባይ እንድትሆን ዘንድ ሀይ ልን እሰጥሀለሁ፣ እና በምድር ላይ ስላለ ችው መንግስቴ ነገሮች በሚመለከት የሁ ሉም ነገሮች እርግጠኛነትን ታውቅ ዘንድ እርሱም ለአንተ [መ]ገላጭ ይሆናል።

፲፪ ስለዚህ፣ በጉዞአችሁ ቀጥሉ እና ልባ ችሁ ይደሰቱ፤ እነሆ፣ እና አስተውሉ፣ እኔ እስከመጨረሻም ከእናንተ ጋር ነኝና።

፲፫ አሁንም [ሠ]ፅዮንን በተመለከት ቃልን እሰጣችኋለሁ። ምንም እንኳን ለጥቂት ዘመን ብትገሰፅም፣ ፅዮን [ረ]ትድናለች።

፲፬ ወንድሞቻችሁ፣ አገልጋዮቼ [ሰ]ኦርሰን ሀይድ እና ጆን ጉልድ፣ በእጆቼ ውስጥ ናቸው፤ እና ትእዛዛቴን እስከጠበቁ ድረስ ይድናሉ።

፲፭ ስለዚህ፣ ልባችሁ ይፅናኑ፤ በቅንነት ለሚራመዱት፣ እና ለቤተክርስቲያኗ ቅድስ እና ጥቅም [ሸ]ሁሉም ነገሮች አብረው ይሰ ራሉና።

፲፮ ለራሴም በፅድቅ የሚያገለግሉኝ [ቀ]ንጹህ ህዝብ አስነሳለሁና፤

፲፯ እና የጌታን ስም [በ]የሚጠሩት፣ እና ትእዛዛቱን የሚጠብቁ ሁሉ ይድናሉ። እን ዲህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፲፩

በታህሳስ ፲፮ እና ፲፯ ፣ ፲፰፻፴፫ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ ኦሀዮ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። በዚህ ጊዜ በሚዙሪ የተሰበሰቡት ቅዱሳን በታላቅ ስደት ላይ ነበሩ። ለአመፅ የተነሱ ህዝብ እነርሱን በጃክሰን የግዛት ክፍል ውስጥ ካሉት ቤቶ

፩ [ሀ] ቅ.መ.መ. ደህንነት።
፪ [ለ] ሉሊ. ፭፡፲፰፣
ት. እና ቃ. ፰፡፰–፲፡፩።
፯ [ሐ] ማቴ. ፲፡፲፱–፳፣
ት. እና ቃ. ፹፩፡፹፡፹፭።
፯ [መ] ቅ.መ.መ. ገር፣ ገርነት።
[ሠ] ት. እና ቃ. ፹፩፡፰፭፬።
፰ [ረ] ፪ ኔፊ ፴፣፡፩–፩።
፱ [ሰ] ዘፀአ. ፩፡፲፡–፲፣
፪ ኔፊ ፫፡፲፣–፲፰፣
ት. እና ቃ. ፻፳፩፡፻፫–፻፩።
፲ [ሸ] ቅ.መ.መ. መመስከር።
፲፩ [ቀ] አልማ ፲፯፡፪–፣።
[በ] ት. እና ቃ. ፻፳፩፡፻፳፭።
፲፣ [በ] ቅ.መ.መ. ፅዮን።
[ተ] ት. እና ቃ. ፹፩፡፶፱፣
፻፳፭፡፱–፲፣ ፴፭፣ ፴፯።
፲፩ [ሀ] ቅ.መ.መ. ሀይድ፣ ኦርሰን።
፲፪ [ለ] ሮሜ ፰፡፳፰፣
ት. እና ቃ. ፶፡፳፩፣ ፻፳፡፴።
፲፯ [ሐ] ቅ.መ.መ. ንጹህ፣ ንጹህነት።
፲፯ [መ] ኢዩ. ፪፡፴፪፣
አልማ ፴፰፡፩–፳።

ቻቸው አሣደዋቸዋል እና አንዳንድ ቅዱሳን ራሳቸውን በቫን ቢዩረን፣ ላፈየት፣ እና ሬይ የግዛት ክፍሎች ውስጥ ለማሰባሰብ ሞከሩ፣ ነገር ግን ስደቱ ተከተላቸው። በዚያ ጊዜ የቅዱሳኑ ዋና ክፍል በክሌይ የግዛት ክፍል ሚዙሪ ውስጥ ነበር። በቤ ተክርስቲያኗ ግለሰቦች ላይም ብዙ የሞት ማስፈራሪያዎች ነበሩ። የኃክሰን የግ ዛት ክፍል ቅዱሳን የቤት እቃዎቻቸውን፣ ልብሶቻቸውን፣ ከብቶቻቸውን፣ እና ሌሎች የግል ንብረቶቻቸውን አጥተው ነበር፤ እና ብዙዎቹም እህሎቻቸውም ተደምስሠውባችው ነበር።

፩–፰፣ ቅዱሳን የተገሰጹት እና የተሰቃዩት በመተላለፋቸው ምክንያት ነው፤ ፱–፲፭፣ የጌታ ቁጣ በህዝብ ላይ ያርፋል፣ ነገር ግን ህዝቦቹ ይሰበሰባሉ እና ይፅናናሉ፤ ፲፮–፳፩፣ ፅዮን እና ስቴኳ ይመሰረታሉ፤ ፳፪–፴፩፣ በአንድ ሺህ አመት ጊዜ ህይወት ምን እንደሚመስል ተገልጿል፤ ፴፪–፴፪፣ በዚ ያም ጊዜ ቅዱሳን ይባረካሉ እናም ዋጋን ይቀበላሉ፤ ፴፫–፴፱፣ የልኡል ሰው እና የወይራ ዛፍ ምሳሌ የፅዮንን ችግር እና የመ ጨረሻም ደህንነትን ያመለክታል፤ ፴፡–፴፡፣ ቅዱሳኑ አብረው መሰብሰባቸውን ይቀጥሉ፤ ፴፪–፴፫፣ ጌታ የዩናትድ ስቴ ትን ህገ መንግስት መሰርቷል፤ ፴፬–፴፭፣ ቅዱሳንን፣ እንደ ሴቷ እና እንዳልጸደቀው ዳኛ ምሳሌ መሰረት፣ ቅዱሳንን ለስቃያ ቸው ክፍያ በቅንነት ይጠይቁ።

፩ ስለተቸገሩት፣ ᵐስለተሰደዱ፣ እና ከውርስ መሬታቸው ᵃተወርውረው ስለወ ጡት ወንድሞቻችሁ እውነት እላችኋለሁ—

፪ እኔ ጌታ ᵐየተሰቃዩበት ስቃይ ᵃበመ ተላለፋቸው ምክንያት እንዲመጣባቸው ፈቅጃለሁ፤

፫ ግን ᵐየእኔ አደርጋቸዋለሁ፣ እና መጥቼ ጌጤን በምሰራበት በዚያን ቀን የእኔ ይሆ ናሉ።

፬ ስለዚህ አንድያ ልጁን ለመስዋት እንዲ ያቀርብ እንደታዘዘው ᵐአብርሐም ᵃመገሰፅና መፈተን አለባቸው።

፭ በግሰጻው የማይጸኑት፣ ግን ᵐየሚ ከዱኝ፣ ሁሉ ᵃሊቀደሱ አይችሉም።

፮ እነሆ፣ እላችኋለሁ፣ ክርክር፣ እና ᵐጸብ፣ እና ᵃቅናት፣ እና ጠብ፣ እና ᵐየመ ቋመጥ እና የመመኘት ፈቃድ በመካከላቸው ነበር፤ ስለዚህ በእነዚህ ነገሮች ውርሶቻቸ ውን በክለዋል።

፯ የጌታ አምላካቸውን ድምፅ ᵐለማድ መጥ ይዘገዩ ነበር፤ ስለዚህ፣ ጌታ አምላካ ቸው ጸሎታቸውን ያደምጥ ዘንድ፣ በችግር ቀናቸውም ይልስላቸው ዘንድ ዘግይቷል።

፰ በሰላም ቀናቸው ምክሬን ትንሽ ዋጋ እንዳለው ተመለከቱት፤ ነገር ግን፣ ᵐበች ግራቸው ቀን፣ ሲያስፈልጋቸው ᵃይፈል ጉኛል።

፱ እውነት እላችኋለሁ፣ ኃጢአቶቻቸው ቢያስቆጡም፣ ለእነርሱ አንጀቴ ᵐበርህ ራሄ ተሞልቷል። ሙሉ ሁሉ ᵃአላስወግዳ ቸውም፤ እና ᵃበቁጣም ቀን በምህረት አስ ታውሳቸዋለሁ።

፲፭ ፩ ᵐ ቅ.መ.መ. ማሳደድ፣ መሳደድ።
ᵃ ት. እና ቃ. ፲፫፡፩–፪፣ ፲፩፡ ፲፱፡ ፴፯።
፪ ᵐ ት. እና ቃ. ፶፰፡፫–፬።
ᵃ ሞዛያ ፯፡ ፳፱–፴፣ ት. እና ቃ. ፲፫፡፬፣ ፲፫፡ ፪–፲።
፫ ᵐ ኢሳ. ፳፡፪፣ ሚል. ፫፡ ፲፯፣ ት. እና ቃ. ፳፡፬።
፬ ᵐ ዘፍጥ. ፳፪፡ ፩–፲፬፣ ያዕቆ. ፬፡ ፭። ቅ.መ.መ. አብርሐም።
ᵃ ት. እና ቃ. ፶፭፡ ፩–፪፣ ፲ ፴፯፣ ፴፩። ቅ.መ.መ. መገሰጽ፣ ተግሳጽ።
፭ ᵐ ማቴ. ፲፡ ፴፪–፴፫፣ ሮሜ ፩፡ ፲፯፣ ፪ ኔፊ ፴፩፡ ፲፬።
ᵃ ቅ.መ.መ. ቅድስና።
፮ ᵐ ቅ.መ.መ. ጸብ።
ᵃ ቅ.መ.መ. ቅናት።
ሐ ቅ.መ.መ. ምኞት።
፯ ᵐ ኢሳ. ፶፱፡ ፪፣ ሞዛያ ፲፩፡ ፳፪–፳፭፣ ፳፩፡ ፲፭፣ አልማ ፭፡ ፴፯።
፰ ᵐ ሔለ. ፲፪፡ ፫።
ᵃ የሐዋ. ፲፯፡ ፳፯፣ አልማ ፴፪፡ ፭–፲፯።
፱ ᵐ ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት፣ ርህራሄ።
ᵃ ኤር. ፴፡ ፲፩።
ሐ ት. እና ቃ. ፶፰፡ ፳፭–፳፪።

፲ መሀላ ገብቻለሁ፣ እና የቁጣዬ [ሀ]ጎራዴ ለህዝቤ እንደሚወድቅ ከዚህ በፊት በሰጠኋችሁ ትእዛዝም መሰረት አዋጁ ወጥቷል፣ እና እንዳልኩትም፣ ይሆናል።

፲፩ ቁጣዬ በሁሉም ህዝብ ላይ ያለሚዛን በቅርብም ይፈሳል፤ እና ይህን የማደርገውም የጥፋታቸው ጽዋ [ሀ]ሲሞላ ነው።

፲፪ እና በዚያ ቀን [ሀ]በመመልከቻ ማማ ላይ የሚገኙት ሁሉ፣ ወይም በሌላ ቃላት፣ የእኔ የሆኑት እስራኤል ሁሉ ይድናሉ።

፲፫ እና የተበተኑት ሁሉ [ሀ]ይሰበሰባሉ።

፲፬ እና [ሀ]የሚያዝኑትም ሁሉ መፅናናትን ያገኛሉ።

፲፭ እና ለስሜ [ሀ]ህይወታቸውን አሳልፈው የሰጡም ሁሉ አክሊል ይጫንላቸዋል።

፲፮ ስለዚህ፣ ፅዮንን በሚመለከት ልባችሁ ይፅናኑ፤ ሁሉም ስጋዎች [ሀ]በእጆቼ ውስጥ ናቸውና፤ ዕረፉ እና እኔም አምላክ እንደሆንሁ [ለ]እወቁ፤

፲፯ ልጆቿ ቢበተኑም፣ [ሀ]ፅዮን ከስፍራዋ አትወጣም።

፲፰ የሚቀሩት እና ንጹህ ልብ ያላቸው፣ ይመለሳሉ እና እነርሱና ልጆቻቸው በዘለአለማዊ ደስታ [ሀ]መዝሙሮች፣ በፅዮን የፈረሱትን [ለ]ለመገንባት [ሐ]ወደውርሳቸው ይመጣሉ—

፲፱ እና እነዚህ ነገሮች ሁሉ ነቢያት ይፈጽሙ ዘንድ ነው።

፳ እነሆም፣ ከመደብኩት [ሀ]ስፍራ በስተቀር የተመደበ ምንም ሌላ ስፍራ የለም፤ ወይም፣ ለቅዱሳን መሰብሰቢያ ስራ፣ ከመደብኩት ስፍራ ሌላ የሚመደብ ምንም ስፍራ የለም—

፳፩ ለእነርሱ በቂ ክፍል የማይገኝበት ቀን እስኪመጣም ድረስ፤ ከዚያም እኔ የምመድብላቸው ሌሎች ስፍራዎች አሉኝ፣ እና ለፅዮን ይጋርዱ እና ብርታቷም ይሆኑ ዘንድ፣ እነዚህም [ሀ]ካስማ ተብለው ይጠራሉ።

፳፪ እነሆ፣ ስሜን የሚጠሩ፣ እና በዘለአለማዊ ወንጌሌ መሰረት የሚያመልኩኝ ሁሉ [ሀ]እንዲሰበሰቡና በተቀደሱ ስፍራዎች [ለ]እንዲቆሙ ፍቃዴ ነው፤

፳፫ እና ለሚመጣው ራዕይም ተዘጋጁ፣ በድንኳኔ ውስጥ፣ ምድርን የሚደብቀው፣ ቤተመቅደሴን የሚሸፍነው [ሀ]መጋረጃ ይወልቃል፣ እና ስጋ ለባሽ ሁሉ በአንድነት [ለ]ያዩኛል።

፳፬ እና [ሀ]የሚበሰብሱ እያንዳንዱ ነገሮች፣ በምድር ላይ የሚኖሩ ሰዎች፣ ወይም የሜዳ እንስሳት፣ ወይም የሰማይ አዕዋፋት፣ ወይም የባሕር ዓሦች ሁሉ [ለ]ይነድዳሉ፤

፳፭ ደግሞም አለቶችም በትልቅ ትኩሳት [ሀ]ይቀልጣሉ፤ እና እውቀቴና [ለ]ክብሬ በምድር ሁሉ እንዲኖሩ፣ ሁሉም ነገሮች [ሐ]አዲስ ይሆናሉ።

፳፮ እና በዚያም ቀን የሰዎች [ሀ]ጥላቻ፣ የእ

፲ ሀ ት. እና ቃ. ፩፥፲፫–፲፬።
፲፩ ሀ ሔለ. ፲፫፥፲፬፤ ኤተር ፪፥፱–፲፩።
፲፪ ሀ ቅ.መ.መ. መጠበቅ፣ ጠባቂ።
፲፫ ሀ ዘዳግ. ፴፥፫–፮፤ ፩ ኔፊ ፲፥፲፬። ቅ.መ.መ. እስራኤል—የእስራኤል መሰብሰብ።
፲፬ ሀ ማቴ. ፭፥፬።
፲፭ ሀ ማቴ. ፲፥፴፱። ቅ.መ.መ. ሰማዕት፣ ሰማዕትነት።
፲፮ ሀ ሙሴ ፮፥፴፪።
ለ ዘፀአ. ፲፬፥፲፫–፲፬፤ መዝ. ፵፮፥፲።
፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. ፅዮን።
፲፰ ሀ ኢሳ. ፴፭፥፲፤ ት. እና ቃ. ፵፭፥፸፩። ቅ.መ.መ. መዘመር።
ለ ዓሞ. ፱፥፲፫–፲፭፤ ት. እና ቃ. ፹፬፥፪–፭፤ ፻፫፥፲፩።
ሐ ት. እና ቃ. ፻፫፥፲፩–፲፬።
፳ ሀ ት. እና ቃ. ፶፯፥፩–፬።
፳፩ ሀ ት. እና ቃ. ፹፪፥፲፫–፲፬፤ ፻፲፭፥፮፣ ፲፯–፲፰። ቅ.መ.መ. ካስማ።
፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. እስራኤል—የእስራኤል መሰብሰብ።
ለ ማቴ. ፳፬፥፲፭፤ ት. እና ቃ. ፵፭፥፴፪፤ ፻፲፭፥፮።
፳፫ ሀ ቅ.መ.መ. ዐይነ-እርግብ።
ለ ኢሳ. ፵፥፭፤ ት. እና ቃ. ፴፰፥፰፤ ፺፫፥፩። ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
፳፬ ሀ ት. እና ቃ. ፳፱፥፳፬።
ለ ሶፎ. ፩፥፪–፫፤ ሚል. ፬፥፩፤ ት. እና ቃ. ፹፰፥፺፬፤ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፴፯።
፳፭ ሀ ዓሞ. ፱፥፭፤ ፪ ጴጥ. ፫፥፲–፲፬። ቅ.መ.መ. ምድር—ምድርን ማፅዳት።
ለ ቅ.መ.መ. አንድ ሺህ አመት።
ሐ ራዕ. ፳፩፥፭።
፳፮ ሀ ኢሳ. ፲፩፥፮–፱። ቅ.መ.መ. ጠላትነት።

ንስሳትም ጥላቻ፣ አዎን፣ የሁሉም ስጋ ለባስ ጥላቻ ከፊቴ ለይቋረጣል።

፳፯ እና በዚያም ቀን ማንም ሰው ያሻውን ቢጠይቅ፣ ይሰጠዋል።

፳፰ እና በዚያም ቀን ሀሰይጣንም ሰውን ለመፈተን ሀይል አይኖረውም።

፳፱ እና ሀሀዘንም አይኖርም ምክንያቱም ሞት የለምና።

፴ በዚያም ቀን ሀህጻን አርጅቶ ካልሆነ በቀር አይሞትም፤ እና ህይወቱም እንደ ዛፍ ህይወት ይሆናል፤

፴፩ እና ሲሞትም አያንቀላፋም፣ ያም በምድር ውስጥ አይቀይም፣ ነገር ግን በቅጽበት ዓይን ሀይለወጣል፣ እና ለይነጠቃል፣ እና ማረፊያውም የከበረ ይሆናል።

፴፪ አዎን፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ጌታ በሚመጣበት በዚያ ሀቀን፣ ሁሉንም ነገሮች ለይገልጣል—

፴፫ ያለፉትን ነገሮች፣ እና ማንም ሰው የማያውቃቸውን ሀየተደበቁ ነገሮችን፣ የምድር ነገሮችን፣ የተሰራበትን፣ እና አላማቸውን እና እቅዳቸውንም ይገልጣል—

፴፬ በጣም ውድ ስለሆኑ ነገሮች፣ ከበላይ ስላሉ ነገሮች፣ እና ከበታች ስላሉ ነገሮች፣ በምድር ውስጥ፣ እና በምድር ላይ፣ እና በሰማይ ውስጥ ስላሉ ነገሮችም ይገልጣል።

፴፭ እና ስለስሜ ሀበመሰደድ የተሰቃዩት ሁሉ፣ እና በእምነት የሚፅናኑት፣ ምንም እንኳን ህይወታቸውን ለስለእኔ እንዲሰጡ ቢጠሩም በዚህ ክብር ሁሉ ተካፋዮች ይሆናሉ።

፴፮ ስለዚህ፣ ሀእስከሞትም አትፍሩ፤ በዚህ አለም ደስታችሁ ሙሉ አይደለምና፣ ነገር ግን በእኔ ለደስታችሁ ሙላት አለው።

፴፯ ስለዚህ፣ ስለሰውነት አታስቡ፣ ወይም ስለሰውነት ህይወት፤ ነገር ግን ሀለነፍስ፣ እና ስለ ነፍስ ህይወትም አስቡ።

፴፰ እና ሀበትዕግስት ነፍሶቻችሁን ታገኙ ዘንድ፣ የጌታን ፊት ዘወትር ለእሹ፣ እና ዘለአለማዊ ህይወትም ይኖራችኋል።

፴፱ ሰዎች ሀወደ ዘለአለማዊ ወንጌሌ ሲጠሩ፣ እና በዘለአለማዊነትም ቃል ኪዳንን ሲገቡ፣ እንደምድር ለጨው እና የሰዎች ጣዕም ሆነው ይቆጠራሉ።

፵ የሰዎች ጣዕም እንዲሆኑም ይጠራሉ፤ ስለዚህ፣ ያ የምድር ጨው ጣዕሙን ካጣ፣ እነሆ፣ ጨውም ከዚያን ጊዜ በኋላ ከንቱ ይሆናል፣ ነገር ግን ይጣላል፣ እናም በሰዎች እግርም ይረገጣል።

፵፩ እነሆ፣ ስለፅዮን ልጆች፣ እንዲሁም ሁሉም ሳይሆን ብዙዎቹን፣ የሚመለከት ጥበብ ይህም ነው፤ ተላላፊዎች ሆነው ተገኝተዋል፣ ስለዚህ ሀመገሰፅም ያስፈልጋቸዋል—

፵፪ ራሱን ሀከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳል፣ ራሱንም ለየሚያዋርድ ከፍ ይላል።

፵፫ አሁንም፣ ስለፅዮን ቤዛነት በሚመለከት ፈቃዴን ታውቁ ዘንድ፣ ምሳሌ አሳያችኋለሁ።

፵፬ አንድ ሀመኮንን በጣም ምርጥ የሆነ ምድር ነበረው፤ እና ለአገልጋዮቹም እንዲህ ይላል፥ ወደ ለወይን ስፍራዬ፣ እንዲሁም ወደዚህ በጣም ወደ ተመረጠ ምድር

፳፮ ለ ቅ.መ.መ. ሰላም።
፳፰ ሀ ራዕ. ፳፥፪–፫፤
፩ ኔፊ ፳፪፥፳፮፤
ት. እና ቃ. ፹፰፥፻፲።
፳፱ ሀ ራዕ. ፳፩፥፬።
፴ ሀ ኢሳ. ፷፭፥፳–፳፪፤
ት. እና ቃ. ፷፫፥፶፩።
፴፩ ሀ ፩ ቆሮ. ፲፭፥፶፪፤
ት. እና ቃ. ፵፫፥፴፪።
ለ ፩ ተሰ. ፬፥፲፮–፲፯።
፴፪ ሀ ት. እና ቃ. ፳፱፥፲፩።
ቅ.መ.መ. አንድ ሺህ አመት።
ለ ት. እና ቃ. ፻፳፩፥፳፮–፳፰።
፴፫ ሀ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ሚስጥሮች።
፴፭ ሀ ት. እና ቃ. ፷፫፥፳።
ቅ.መ.መ. ማሳደድ፣ መሳደድ።
ለ ት. እና ቃ. ፺፰፥፲፫።
፴፮ ሀ ቅ.መ.መ. ስጋዊ ሞት።
ለ ቅ.መ.መ. ደስታ።
፴፯ ሀ ቅ.መ.መ. ነፍስ።
፴፰ ሀ ቅ.መ.መ. ትዕግስት።
ለ ፪ ዜና ፯፥፲፬፤
ት. እና ቃ. ፺፫፥፩።
፴፱ ሀ ቅ.መ.መ. አዲስ እና የዘለአለም ቃል ኪዳን።
ለ ማቴ. ፭፥፲፫፤
ት. እና ቃ. ፻፫፥፲።
፵፩ ሀ ቅ.መ.መ. መገሰጽ፣ ተግሳጽ።
፵፪ ሀ አብድ. ፩፥፫–፬፤
ሉቃ. ፲፬፥፲፩፤
ሔለ. ፬፥፲፪–፲፫።
ለ ሉቃ. ፲፰፥፲፬።
ቅ.መ.መ. ትሁት፣ ትሕትና።
፵፬ ሀ ት. እና ቃ. ፻፫፥፳፩–፳፪።
ለ ቅ.መ.መ. የጌታ የወይን አትክልት ስፍራ።

ሂዱ፣ እና አስራ ሁለት የወይራ ዛፎችንም ትከሉ፤

፵፭ እና ጠላት ለማጥፋትና የወይን ስፍራዬን ፍሬ ለራሳቸው ለመውሰድ ሲመጡ፣ የወይራ ዛፎቼን እንዳይሰበሩ ዘንድ፣ በማማው ላይ [ሀ]ጠባቂዎች ይሆኑላችሁ ዘንድ፣ በአካባቢያቸውም ጠባቂዎችን አኑሩ፣ እና በዙሪያውም የሚገኘውን ምድር በሚመለከት ማማን ስሩ።

፵፮ አሁን፣ የመኮንኑ አገልጋዮች ጌታቸው እንዳዘዛቸው ሄደው አደረጉ፣ እና የወይራ ዛፎችን ተከሉ፣ እና በዙሪያም ቅጥርን ሰሩ፣ እና ጠባቂም አስቀመጡ፣ እና ማማ መስራትም ጀመሩ።

፵፯ እና የዚህን መሰረት እየገነቡ እያሉ፣ እርስ በራሳቸው እንዲህ መባባል ጀመሩ፥ ለጌታዬ ይህ ማማ ምን ይሰራለታል አለው?

፵፰ እና ለብዙም ጊዜ እርስ በራሳቸው እንዲህ በመባባል ተማከሩ፥ የሰላም ጊዜ እንደሆነ እያየ፣ ጌታዬ ከዚህ ማማ ምን ጉዳይ አለው?

፵፱ ገንዘቡ ለለዋጮች አደራ ቢሰጥ አይሻልምን? ለእነዚህ ነገሮች ምንም የሚያስፈልጉ አይደሉምና።

፶ እና እርስ በራሳቸው ባለመስማማት እያሉ በጣም ሀኬተኛ ሆኑ፣ እና የጌታቸውንም ትእዛዝ አላደመጡምና።

፶፩ እና ጠላትም በምሽት መጣ፣ እና [ሁ]ቅጥሩንም ሰበረ፤ እና የመኮንኑ አገልጋዮችም ተነሱ እና ፈሩ፣ እና ሸሹ፤ እና ጠላትም ስራቸውን አፈረሰው፣ እና የወይራ ዛፎችንም ሰበረ።

፶፪ አሁን፣ እነሆ፣ መኮንኑ፣ የወይኑ ስፍራ ጌታ፣ አገልጋዮቹን ጠራ፣ እናም አላቸው፣ ለምን! የዚህ ታላቅ ጥፋት ምክንያት ምንድን ነው?

፶፫ እና የወይን ስፍራውን ከተከላችሁ፣ እና አጥርንም በዙሪያው ካጠራችሁ፣ እና በግምቡ ላይ ጠባቂን ካስቀመጣችሁ በኋላ ማማን ስሩ፣ እና በማማውም ጠባቂን አስቀምጡ፣ እና የወይን ስፍራዬንም ጠብቁ፣ እና ጠላትም እንዳይመጣባችሁ አታንቀላፉ ብዬ እንዳዘዝኳችሁ አታደርጉም ነበርን?

፶፬ እነሆም፣ በማማው ላይ የነበረው ጠባቂ በሩቅ እያለ ጠላትን ገና በሩቅ ሳለ ያየው ነበር፤ ከዚያም ትዘጋጁ እና ጠላትንም አጥሩን ከመስበር ልታቆሙት፣ እና ከደምሳሹ እጆችም የወይን ስፍራዬን ልታድኑ በቻላችሁ ነበር።

፶፭ እና የወይን ስፍራው ጌታ ከአገልጋዮቹ ለአንዱ አለ፥ ሂድ እና የሚቀሩትን አገልጋዮቼን ሰብስብ፣ እና የቤቴ ብርታት የሆኑትን ጀግኖቼን፣ ወጣት ወንዶቼን፣ እና ከአገልጋዮቼ መካከልም ጎልማሳዎች የሆኑትን የቤቴን ብርቱዎች [ሁ]ሉ ውሰድ፣ እንዲቀሩ የመደብኳቸውን ብቻ አስቀር፤

፶፮ እና በቀጥታም ወደወይን ስፍራ መሬቴም ሂድ፣ እና የወይን ስፍራዬን አድን፤ የእኔ ነውና፤ በገንዘብም ገዝቼዋለሁና።

፶፯ ስለዚህ፣ ወደ መሬቴ በቀጥታ ሂድ፣ የጠላቶቼን ግንብ ስበር፤ ማማቸውንም ጣል፣ እና ጠባቂያቸውንም በትን።

፶፰ እና አንተን ለመቃወም እስከተሰበሰቡ ድረስ፣ በአጭር ጊዜ ከሚቀረው ቤቴ ጋር መጥቼና መሬቴን እንድወስደው ዘንድ፣ በጠላቶቼ ላይ [ሀ]ፍረድልኝ።

፶፱ እና አገልጋዩም ለጌታው አለ፥ እነዚህ ነገሮች መቼ ይሆናሉ?

፷ እና ለአገልጋዩም አለ፥ በቀጥታ ሂድ፣ እና እንደፈቀድኩትም ያዘዝኩህን ማንኛቸውን ነገሮች ሁሉ አድርግ፤

፷፩ እና ይህም—በቤቴ መካከል ታማኝና ብልህ [ሀ]መጋቢ፣ በመንግስቴም ውስጥ [ለ]ገዢ በሆንከው በአንተ ላይ ማህተሜ እና በረከቴ ይሆናል።

፵፭ ሀ ሕዝ. ፴፫፡፪፣ ፯፤ ፮ ኤፌ ፲፯፡፲፰። ቅ.መ.መ. መጠበቅ፣ ጠባቂ።
፶፩ ሀ ኢሳ. ፭፡፩–፯።
፶፭ ሀ ት. እና ቃ. ፲፫፡ ፳፪፣ ፳፱–፴፣ ፲፭፡ ፲፯፣ ፳፱–፴።
፶፮ ሀ ት. እና ቃ. ፯፲፯፡ ፳፪–፳፬፤
፶፯ ሀ ት. እና ቃ. ፫፡ ፲፭።
፶፰ ሀ ት. እና ቃ. ፫፫፡ ፳፪።
ለ ማቴ. ፳፭፡ ፳–፳፫።

፳፪ እና አገልጋዩም በቀጥታ ሄደ፣ እና ጌታው ያዘዘውን ማንኛቸውን ነገሮች ሁሉ አደረገ፤ እና ከብዙ ቀናትም ᵐበኋላ ሁሉም ነገሮች ተፈጸሙ።

፳፫ ዳግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ በትክክል እና በተገቢ መንገድ ወደ ደህንነታቸው ለመመራት ፈቃደኛ እስከሆኑ ድረስ፣ ስለቤተክርስቲያናት ሁሉ የሚመለከት ጥበቤን አሳያችኋለሁ—

፳፬ የቅዱሳኖቼ መሰብሰቢያ ስራ ይቀጥል ዘንድ፣ በስሜም ᵐበቅዱስ ቦታዎች እገነባቸው ዘንድ፤ ᵃየመከር ጊዜ መጥቷል፣ እና ቃሌም ʰመፈጸም አለበት።

፳፭ ስለዚህ፣ ወደአባቴ መንግስት እንደ ስራው ደመወዝን ልሰጠው ስመጣ፣ በስን ዴዎች እና ᵐእንክርዳዶች ምሳሌ መሰረት፣ ስንዴዎች በጎተራው እንዲሰበሰቡ እና የዘለአለም ህይወት ያገኙ ዘንድ፣ እና ᵃበሰለስቲያል ክብር አክሊል እንዲሰጣቸው፣ ህዝቤን መሰብሰብ አለብኝ፤

፳፮ በማይጠፋ እሳት ᵐይቃጠሉ ዘንድ፣ እንክርዳዶችም አንድ ላይ ይታሰራሉ፣ እና ማሰሪአቸውም ጠንካራ ይሆናል።

፳፯ ስለዚህ፣ በመደብኩት ስፍራ አብረው ለመሰብሰብ ይቀጥሉ ዘንድ፣ ለሁሉም ቤተ ክርስቲያኖች ትእዛዝን እሰጣለሁ።

፳፰ ይህም ቢሆን፣ በፊቱ ትእዛዝ እንዳልኳችሁ፣ ᵐመሰብሰቢያችሁ በችኮላ ወይም በሽሽት አይሁን፤ ነገር ግን በፊታችሁ ሁሉም ነገሮች ይዘጋጁ።

፳፱ እና ሁሉም ነገሮች በፊታችሁ ይዘጋጁ ዘንድ፣ ስለእነዚህ ነገሮች የሰጠኋች ሁን ትእዛዝ አክብሩ—

፴ እንዲህ ያለውን ወይም የሚያስተምረ ውን፣ ለቅዱሳኔ መሰብሰብ መጀመሪያ እን ዲሆን፣ የፅዮን ምድር እንዲሆን በመደብ ኩት ምድር አካባቢ በገንዘብ ለመገዛት የሚ ቻለውን መሬቶችን ሁሉ በገንዘብ ᵐለመ ግዛት ያለውን ወይም የሚያስተምረውን፤

፴፩ በጃክሰን የግዛት ክፍል፣ እና በዙ ሪያው በሚገኙት የግዛት ክፍሎች፣ ሊገዛ የሚቻለውን መሬት ሁሉ፣ እና የሚቀረ ውን በእጄ ተዉት።

፴፪ አሁን እውነት እላችኋለሁ፣ ሁሉም ቤተክርስቲያናት ገንዘባቸውን ሁሉ አብ ረው ይሰብስቡ፤ ᵐበችኮላ ሳይሆን፣ እነዚህ ነገሮች ሁሉ በጊዜአቸው ይደረጉ፤ እና በፊ ታቸሁ ሁሉንም ነገሮች እንዲዘጋጁ አድ ርጉ።

፴፫ እና የተከበሩ ሰዎች፣ እንዲሁም ብልህ ሰዎች፣ ይመደቡ፣ እና እነዚህን መሬቶች እንዲገዙ ላኳቸው።

፴፬ እና በምስራቅ አገሮች ያሉ ቤተክ ርስቲያናትም፣ ከተመሰረቱ በኋላ፣ ይህን ምክር ካደመጡ መሬቶችን መግዛትና መሰ ብሰብ ይችላሉ፤ እና በዚህም መንገድ ፅዮ ንን ይመስርቱ።

፴፭ አሁንም፣ በስሜ የሚጠሩት ቤተክር ስቲያናት ድምጼን ለማድመጥ ᵐፈቃደኞች ቢሆኑ፣ ፅዮንን ለማዳን እና፣ ደግሞም እን ዳይጣሉ የፈረሱትን ስፍራዎቿን ለመመ ስረት በብቁ፣ እንዲሁም በሚትረፈረፍ፣ ተከማችቷል።

፴፮ ደግሞም እላችኋለሁ፣ በጠላቶቻቸው የተበተኑትም እንደገገር በተመደቡት እጆች እና በእናንተ ላይ ስልጣን ባላቸው ሰዎች በኩል ለስቃያቸው ክፍያ፣ እና ለቤዛነት በቅንነት እንዲጠይቁ ፍቃዴ ነው—

፴፯ የፅድቅ እና ቅዱስ በሆኑ መሰረታዊ መርሆች፣ እንዲመሰረት እና ለሁሉም ስጋ ለባሽ ᵐመብት እና ጥበቃ እንዲደገፍ በፈ ቀድኩት በህዝብ ህግጋት እና ᵃህገ መንግ ስት መሰረት፤

፴፰ ሁሉም ሰው ስለወደፈቱ፣ በሰጠሁት

፳፪ ᵐ ት. እና ቃ. ፲፭፡ ፴፯።
፳፬ ᵐ ት. እና ቃ. ፹፯፡ ፳።
ᵃ ት. እና ቃ. ፴፫፡ ፫፡ ፯።
ᵇ ቅ.መ.መ. መካር።
ʰ ት. እና ቃ. ፭፡ ፴፳።
፳፭ ᵐ ማቴ. ፲፫፡ ፮–፴፫፤
ት. እና ቃ. ፹፯፡ ፭–፮።
ᵃ ቅ.መ.መ. የሰለስቲያል ክብር።
፳፮ ᵐ ናሆ ፭፡ ፭፤ ማቴ. ፫፡ ፲፪፤
ት. እና ቃ. ፴፯፡ ፲፪፤
፳፫፡ ፴፫–፴፬።
፳፯ ᵐ ት. እና ቃ. ፱፮፡ ፱–፲።
ᵃ ት. እና ቃ. ፴፯፡ ፭–፮።
ᵐ ት. እና ቃ. ፳፫፡ ፲–፲፪።
ᵃ ቅ.መ.መ. ክብር።
ᵐ ት. እና ቃ. ፳፫፡ ፳–፳፩።
ᵃ ᵐ ት. እና ቃ. ፳፫፡ ፳፯–፳፱።
ᵐ ᵐ ኢሳ. ፶፪፡ ፲–፲፪።
ᵐ ᵐ አልማ ፭፡ ፴፯–፴፱።
ᵐ ᵐ ቅ.መ.መ. መብት።
ᵃ ቅ.መ.መ. መንግስት።

ስነምግባር [ሀ]ምርጫ መሰረት፣ በትምህርትና በመሰረታዊ መርሆችም ይሰራ ዘንድ፣ እያንዳንዱም ሰው ለራሱ ኃጢአቶች [ለ]በፍርድ ቀን [ሐ]ይጠየቅበት ዘንድ ለቤዛነት በቅንነት እንዲጠይቁ ፍቃዴ ነው።

፸፱ ስለዚህ፣ ማንም ሰው ለሌላ በባሪያነት መተሳሰሩ ትክክል አይደለም።

፹ እና ለዚህ አላማ የዚህን [ሀ]ህገ መንግስት፣ ለዚህ አላማ ባነሳኋቸው የጥበብ ሰዎች እጅ አማካይነት፣ መስርቼአልሁ እና ምድሩንም ደም [ለ]በማፍሰስ አድኜዋለሁ።

፹፩ አሁን፣ የፅዮን ልጆችን ከምን ጋር አመሳስላቸዋለሁ? ሰዎች ሳይታክቱ ዘወትር [ሀ]መጸለይ አለባቸውና፣ እንዲህ ከሚለው የሴቷ እና ፍትሀዊ ያልሆነ ዳኛ [ለ]ምሳሌ ጋር አመሳስላቸዋለሁ—

፹፪ በአንዲት ከተማ እግዚአብሔርን የማይፈራ ሰውንም የማያፍር አንድ ዳኛ ነበር።

፹፫ በዚያችም ከተማ አንዲት መበለት ነበረች፣ ወደ እርሱም እየመጣች ከጠላቴ ፍረድልኝ ትለው ነበር።

፹፬ ለአያሌ ቀንም ይህን ያደርግ ዘንድ አልወደደም፣ ከዚህ በኋላ ግን በልቡ፥ ምንም እግዚአብሔርን ባልፈራ ሰውንም ባላፍር፣ ይህች መበለት ስለምታደክመኝ ዘወትር እየመጣች እንዳታውከኝ እፈርድላታለሁ አለ።

፹፭ የፅዮንንም ልጆች በዚህም እመስላቸዋለሁ።

፹፮ በዳኛው እግር ላይም በቅንነት ይማጸኑ፤

፹፯ እና ካልሰማቸውም፣ በአስተዳዳሪው እግር ላይም በቅንነት ይማጸኑ፤

፹፰ አስተዳዳሪውም የማያደምጣቸው ከሆነ፣ በፕሬዘደንት እግር ላይም በቅንነት ይማጸኑ፤

፹፱ ፕሬዘደንቱም የማያደምጣቸው ከሆነ፣ ከዚያም ጌታ ይነሳል እና [ሀ]ከተሰወረበትም ስፍራ ይመጣል፣ እና በንዴቱም ህዝብን ያስጨንቃቸዋል፤

፺ በመዓቱም፣ እና በሀይለኛ ቁጣው፣ በጊዜው ክፉዎችን፣ ታማኝ ያልሆኑትን፣ እና ጻድቅ ያልሆኑትን [ሀ]መጋቢዎች ያገልላል፣ እና እድላቸውንም ከግብዞችና [ለ]ከማያምኑት ጋር ያደርግባቸዋል፤

፺፩ እንዲሁም በዚያ [ሀ]ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት በሆነበት፣ ወደ ድቅድቅ ጨለማ።

፺፪ ስለዚህ ጆሮዎቻቸው ለልቅሶዎቻችሁ ይከፈቱ ዘንድ፣ እኔ ለእነርሱ [ሀ]መሀሪ እሆን ዘንድ፣ እነዚህም ነገሮች እንዳይመጣባቸው ጸልዩ።

፺፫ ሁሉም ሰዎች [ሀ]ያለምክንያት ይቀሩ ዘንድ፣ ያልኳችሁ ሁሉ መፈጸም አለባቸው፤

፺፬ ብልህ ሰዎች እና መሪዎች [ሀ]ያላሰቧቸውን ነገሮች ይሰሙ እና ያውቁ ዘንድ መሆን አለባቸው፤

፺፭ ስራዬን ለማምጣት፣ እና ስራዬን፣ ማለት [ሀ]እንግዳ ስራዬን፣ እቀጥል ዘንድ፣ ሰዎችም በጽድቅ እና ኃጢአት መካከል [ለ]ለመለየት ይችሉ ዘንድ ነው፣ ይላል ጌታ።

፺፮ ደግሞም፣ እላችኋለሁ፣ አገልጋዬ ስድኒ ጊልበርት ለህዝቤ የመደብኩትን [ሀ]የጎተራ ስፍራዬን ወደ ጠላቶቼ እጆች ውስጥ መሸጡ ትእዛዜን እና ፈቃዴን የሚቃረን ነው።

፸፰ ሀ ቅ.መ.መ. ነጻ ምርጫ።
ለ ቅ.መ.መ. ፍርድ፣ የመጨረሻው።
ሐ ቅ.መ.መ. መልስ መስጠት፣ ሂሳብ፣ ተጠያቂነት፣ ሀላፊነት።
፹ ሀ ፪ ኔፊ ፩፥፯–፱፤ ት. እና ቃ. ፺፰፥፭–፯። ቅ.መ.መ. ህገ መንግስት።
ለ ፩ ኔፊ ፲፫፥፲፫–፲፱።
፹፩ ሀ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
ለ ሉቃ. ፲፰፥፩–፰።
፹፱ ሀ ኢሳ. ፵፭፥፲፭፤ ት. እና ቃ. ፻፳፩፥፩፣ ፬፤ ፻፳፫፥፮።
፺ ሀ ቅ.መ.መ. መጋቢ፣ መጋቢነት።
ለ ራዕ. ፳፩፥፰። ቅ.መ.መ. አለማመን።
፺፩ ሀ ማቴ. ፳፭፥፴፤ ት. እና ቃ. ፲፱፥፭፤ ፳፱፥፲፭–፲፯፤ ፻፳፬፥፰።
፺፪ ሀ ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።
፺፫ ሀ ሮሜ ፩፥፲፰–፳፩።
፺፬ ሀ ኢሳ. ፶፪፥፲፭፤ ፫ ኔፊ ፳፥፵፭፤ ፳፩፥፰።
፺፭ ሀ ኢሳ. ፳፰፥፳፩፤ ት. እና ቃ. ፺፭፥፬።
ለ ሚል. ፫፥፲፰። ቅ.መ.መ. የመለየት ስጦታ።
፺፮ ሀ ቅ.መ.መ. ጎተራ።

፲፯ በጠላቶቼ፣ ራሳቸውንም በስሜ ᐸበሚ ጠሩት ፈቃድ፣ እኔ የመደብኩት ይራከስ ዘንድ አትፍቀዱ።

፲፰ ይህም በእኔና በህዝቤ ላይ የተደረገው ከፍተኛ እና አሳዛኝ ኃጢአት ነውና፣ በዚ ህም ምክንያት በአህዛብ ላይ በቅርብ የሚወ ድቁትን እነዚያን ነገሮች አውጃለሁ።

፲፱ ስለዚህ፣ ምንም እንኳን እንዲኖሩ ባቸው ባይፈቀድላቸውም፣ ህዝቤ ለእነ ርሱ የመደብኩላቸውን እንደገና እንዲ ይዙ፣ እና በመብትም እንዲይዙ ፍቃዴ ነው።

፳ ይህም ቢሆን፣ በዚያ አይኖሩም አላ ልኩም፤ ለመንግስቴ ብቁ የሆኑ ፍሬዎችና ስራዎች እስካመጡ ድረስ በእነዚያም ላይ ይኖራሉ።

፳፩ ይገነባሉ፣ እና ሌላም ᐸአይወርሰ ውም፤ የወይን ስፍራንም ይተክላሉ፣ እና የእነዚህን ፍሬዎቻቸውንም ይበላሉ። እን ዲህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፲፪

በየካቲት ፲፯፣ ፲፰፻፴፬ (እ.አ.አ.) የቤተክርስቲያኗ የመጀመሪያ ከፍተኛ ሽንጎ ሲመሰረት የተያዘ ቃለጉባኤ። የመጀመሪያዎቹ ቃለጉባኤዎች በሽማግሌዎች ኦሊ ቨር ካውድሪ እና ኦርሰን ሀይድ የተጻፉ ነበሩ። ነቢዩ ቃለጉባኤዎችን በሚቀጥለው ቀን አስተካከለ፣ እናም የተስተካከሉት ቃለጉባኤዎች በሚቀጥለው ቀን በከፍ ተኛ ሽንጎዎች "እንደ ቤተክርስቲያኗ መልክ እና ህገ መንግስት" በሙሉ ስምም ነት ተቀባይነትን አገኙ። ይህ ክፍል በትምህርት እና ቃል ኪዳን ህትመት ሲዘ ጋጅ፣ ስለአስራ ሁለቱ ሐዋሪያት ቡድን የሆኑት ከፀ እስከ ፀ፪ ቁጥሮች በ፲፰፻፴፭ (እ.አ.አ.) በጆሴፍ ስሚዝ አመራር ተጨመሩ።

፩–፰፣ ከፍተኛ ሽንጎ በቤተክርስቲያኗ ውስጥ የሚነሱ አስቸጋሪ ጉዳዮች መፍ ትሄ ለማግኘት ተመድቧል፤ ፱–፲፰፣ ለሚቀርቡ ጉዳዮች ስነስርዓቶችም ተሰ ጥተዋል፤ ፲፱–፳፫፣ የሽንጎው ፕሬዘደንት የሚገባ ውሳኔን ይሰጣል፤ ፳፬–፳፱፣ የይገ ባኝ ስነስርዓትም ተሰጥቷል።

፩ በዚህ ቀን ሀያ አራት የአጠቃላይ ሽንጎ ሊቀ ካህናት በጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ ቤት ውስጥ በራዕይ ተሰበሰቡ፣ እና አስራ ሑለት ሊቀ ካህናት እና፣ ጉዳዩ እንደሚያስፈል ገው አንድ ወይም ሶስት ፕሬዘደንት ያለ ውን የክርስቶስ ቤተክርስቲያንን ᐸከፍተኛ ሽንጎ ማደራጀት ጀመሩ።

፪ ከፍተኛ ሽንጎውም፣ ቤተክርስቲያኗ ወይም ᐸየኤጲስ ቆጶስ ሽንጎ በጉዳዩ የነበሩ ትን ሁሉ በማርካት መፍትሄ ለማግኘት የማ ይቻሉትን፣ በቤተክርስቲያኗ ውስጥ ሊነሱ በሚችሉ አስፈላጊ ችግሮች ላይ መፍትሄ ለማግኘት በራዕይ ተመድቧል።

፫ ጆሴፍ ስሚዝ፣ ዳግማዊ፣ ስድኒ ሪግደ ንና ፍሪድሪክ ጂ ዊሊያምስ በሽንጎው ድምፅ እንደ ፕሬዘደንቶች ተረጋግጠው ነበር፤ እና ሊቀ ካህናት ጆሴፍ ስሚዝ፣ ቀዳማዊ፣ ጆሴፍ ኮ፣ ጆን ዊትመር፣ ማርቲን ሀሪስ፣ ጆን ኤስ ካርተር፣ ጀርድ ካርተር፣ ኦሊቨር ካውድሪ፣ ሳሙኤል ኤች ስሚዝ፣ ኦርሰን ሀይድ፣ ስይልቨስተር ስሚዝ፣ እና ሉክ ጆንሰን ለቤተክርስቲያኗ ቋሚ ሽንጎ በመ ሆን፣ በሽንጎው በአንድ ድምፅ ተመርጠው ነበር።

፬ ከዚያም ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ሽንጎ ዎች የተመደቡበትን እንደሚቀበሉ፣ እና

፲፯ ᐸ ት. እና ቃ. ፲፫፡፬፣ ፲፣ ፲፣ ፲፪፡፳፭–፳፮፣ ፲፳፭፡፳፭–፳፮፣ ፲፳፭፡፪። ፲፭ ᐸ ኢሳ. ፳፭፡፳፭–፳፱። ቅ.መ.መ. አንድ ሺህ አመት። ፲፱ ፩ᐸ ቅ.መ.መ. ከፍተኛ ሽንጎ። ፪ᐸ ት. እና ቃ. ፲፯፡፫–፴፪።

በሰማይ ህግ መሰረት በዚያም ሀላፊነት እን ደሚሰሩ ተጠይቀው ነበር፣ ለዚህም የተመ ደቡበትን እንደሚቀበሉ፣ እና ሀላፊነታቸ ውን በተሰጣቸው በእግዚአብሔር ጸጋ መሰ ረት እንደሚፈፅሙም መልስ ሰጡ።

፭ ከላይ የተጠቀሱትን ሽንጎዎች ለመመ ደብ በቤተክርስቲያኗ ስም እና ለቤተክርስ ቲያኗ ድምጻቸውን የሰጡት ሽንጎዎች ቁጥር እንደሚከተለው ነበሩ፥ አርባ ዘጠኝ ሊቀ ካህናት፣ አስራ ሰባት ሽማግሌዎች፣ አራት ካህናት፣ እና አስራ ሶስት አባላት።

፮ ድምፅ ሰጡ፥ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ሽንጎዎች፣ ወይም በእነርሱ ወኪል የተመ ደቡት ምትኮች ሰባቱ ካልተገኙ በስተቀር ከፍተኛ ሽንጎው ለመስራት ሀይል ሊኖረው አይችልም።

፯ እነዚህ ሰባቱም ብቁ እና ሽንጎዎቹ በማ ይኖሩበት ጊዜ በእነርሱ ምትክ ለመስራት ችሎታ አላቸው ብለው የሚያስቡአቸውን ሌሎች ሊቀ ካህናትን ለመመደብ ሀይል አላ ቸው።

፰ ድምፅ ሰጡ፥ ከላይ የተጠቀሱት ማንኛ ቸውም ሽንጎዎች በሞት፣ በመተላለፍ ምክ ንያት ከሀላፊነት ቢወገዱ፣ ወይም ከቤተ ክርስቲያኗ መንግስት አካባቢ በመውጣት በመወገድ ምክንያት ክፍተት ቢኖር፣ በፕ ሬዘደንቱ ወይም ፕሬዘደንቶቹ ጥቆማ፣ እና ለዚህ አላማ በቤተክርስቲያኗ ስም ለመስ ራት በተሰበሰቡት በሊቀ ካህናቱ ከፍተኛ ሽንጎ ድምፅ ቅበላ ይህም ስፍራ ይሞላል።

፱ የሽንጎው ፕሬዘደንት የሆነው የቤተክር ስቲያኗ ፕሬዘደንት የሚመደበው [1]በራዕይ ነው፣ እና በቤተክርስቲያኗም ድምፅ አስ ተዳደሪነቱ እውቅና [2]ይሰጠው።

፲ እና ይህም በሀላፊነቱ ክብር ምክን ያት በቤተክርስቲያኗ ሽንጎ ይሰየማል፤ እና እርሱ በመተደበበት አይነት በተመደቡት ሁለት ሌሎች ፕሬዘደንቶች ይረዳ ዘንድም መብቱ ነው።

፲፩ እንዲረዱት የተመደቡት አንዱ ወይም ሁለቱ የማይኖሩ ቢሆን፣ ካለረዳቶቹ ሽንጎን ለመምራት ሀይል አለው፤ እና እርሱም ባይኖር፣ ሌሎቹ፣ ከሁለቱ አንዱ ወይም ሁለቱም ፕሬዘደንቶች በእርሱ ስፍራ ለመ ምራት ይችላሉ።

፲፪ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ከፍተኛ ሽንጎ በትክክለኛው አሰራር በየጊዜው በሚደራጅበት ጊዜ፣ አስራ ሁለቱ ሽንጎ ዎች ምርጫን በእጣ የመወሰን ሀላፊነት አላቸው፣ በዚህም፣ ከቁጥር አንድ ጀምሮ ተከታትሎ እስከ አስራ ሁለት ድረስ፣ ከአ ስራ ሁለቱ የትኛው አስቀድሞ እንደሚና ገር ይወሰናሉ።

፲፫ በማንኛውም ጉዳይ ላይ ለመስራት ሽንጎው ሲሰበሰብ፣ አስራ ሁለቱ ሽንጎዎች ጉዳዩ አዳጋች መሆን አለመሆን ያስቡበት፤ ይህ ካልሆነ፣ ከላይ በተጻፈው ምሳሌ መሰ ረት ሁለት የሽንጎው አባላት ብቻ ይነጋገ ሩበታል።

፲፬ ነገር ግን አስቸጋሪ እንደሚሆን የሚታ ሰብበት ከሆነ፣ አራት ይመደባሉ፤ ከዚያም በላይ አስቸጋሪ ከሆነም፣ ስድስት፤ ነገር ግን በማንኛውም ጉዳይ ከስድስት በላይ እንዲ ናገሩ አይመደቡም።

፲፭ በሁሉም ጉዳዮች፣ ስድብ ወይም ግፍን አስቀድሞ ለመከላከል፣ ተከሳሹ በሽንጎው ግማሽ አባላት የመዳኘት መብት አለው።

፲፮ እና በሽንጎው ፊት ለመናገር የተመደ ቡት አማካሪዎች፣ ማስረጃው ከተመረመረ በኋላ፣ በእውነት ግልጽ ጉዳዩን በሽንጎው ፊት ያቅርቡ፤ እና እያንዳንዱም ሰው በእ ኩልነት እና [3]በፍትህዊነት መሰረት ይናገር።

፲፯ ሙሉ ቁጥሮችን የያዙ፣ ማለትም ፪፣ ፬፣ ፮፣ ፰፣ ፲፣ ፲፪ እና ፲፪ን የመረጡት አማካ ሪዎች ለተከሰሰው ሰው የሚቆሙለት፣ እና ስደብ ወይም ግፍን አስቀድሞ የሚከላከሉ ግለሰቦች ናቸው።

፲፰ በሁሉም ጉዳዮች፣ መረጃዎቹ ከተ ሰሙ እና በጉዳዩ እንዲናገሩ የተመረጡት

[1] ሀ ቅ.መ.መ. ራዕይ።
ለ ቅ.መ.መ. የቤተክርስቲያን መሪዎችን መደገፍ።
[2] ሀ ቅ.መ.መ. ፍትህ።

አማካሪዎች ንግግራቸውን ከፈጸሙ በኋላ፣ የተከሰሰው እና ከሳሹ በሽንጎው ፊት ለራሳ ቸው ለመናገር መብት አላቸው።

፲፱ መረጃዎቹ ከተሰሙ በኋላ፣ አማካሪ ዎቹ፣ ከሳሹ፣ እና ተከሳሹ ከተናገሩ በኋላ፣ ፕሬዘደንቱ በጉዳዩ ባለው መረጃ መሰረት ውሳኔ ይሰጣል፣ እና አስራ ሁለቱን አማካ ሪዎችንም ይህን በምርጫቸው እንዲቀበሉ ይጠራቸዋል።

፳ ነገር ግን፣ መረጃውን እና ያለገለልተ ኛነት አቤቱታውን ከሰሙ በኋላ፣ የሚቀ ሩት ያልተናገሩት አማካሪዎች ወይም ማን ኛቸውም በፕሬዘደንቱ ውሳኔ ስህተት ቢያ ገኙ፣ ይህንንም ይግለጹ፣ እና ጉዳዩም እን ደገና ይቀርባል።

፳፩ እና በጥንቃቄ እንደገና ከሰሙት በኋላ፣ ተጨማሪ ብርሀን በጉዳዩ ላይ ከታየ፣ በዚህም መሰረት ውሳኔው ይቀየር።

፳፪ ምንም ተጨማሪ ብርሀን ባልተሰጠ በት ጉዳይ ግን፣ የሽንጎ አብላጫው እንደ ነበረ የመወሰን ሀይል ስላለው፣ የመጀመሪ ያው ውሳኔ አይለወጥም።

፳፫ [ሀ]ትምህርትን ወይም መሰረታዊ መር ህን በሚመለከት የችግር ጉዳይ፣ ለሽንጎ ውን አዕምሮዎች ጉዳዩን ግልፅ ለማድረግ ብቁ ፅህፈት ባይኖር፣ ፕሬዘደንቱ መጠ የቅ እና የጌታን አስተሳሰብ [ለ]በራዕይ ለማ ግኘት ይችላል።

፳፬ ሊቀ ካህናት፣ በውጪ እያሉ፣ ከዚህ በፊት እንደ ተመደበው፣ ሰዎቹ ወይም እያ ንዳንዳቸው ሲጠይቁ ለችግሮች መፍትሄ ለማግኘት ሽንጎን ለማደራጀት እና ለመጥ ራት ሀይል አላቸው።

፳፭ እና የተጠቀሰውም የሊቀ ካህናት ሽንጎ ከቁጥራቸው አንዱን በዚህ አይነት ሽንጎ ላይ ለጊዜው እንዲመራ ለመመደብ ሀይል አላቸው።

፳፮ ወዲያውም የሽንጎ ሂደታቸውን፣ ከውሳኔአቸው ጋር ሙሉ ምስክርን አያ ይዘው፣ ለቤተክርስቲያኗ ቀዳሚ አመራር ከፍተኛ ሽንጎ መቀመጫ የመላክ ሀላፊነትም ለተጠቀሱት ሽንጎዎችም ነው።

፳፯ ሰዎቹ ወይም እያንዳንዳቸው በተ ጠቀሱት ሽንጎ ውሳኔ የማይደሰቱ ቢሆን፣ ለቤተክርስቲያኗ ቀዳሚ አመራር ከፍተኛ ሽንጎ መቀመጫ ይገባኝ ለማቅረብ እና የምስክር ቃል ዳግም ሊያሰሙ ይችላሉ፣ ይህም ጉዳይ ከዚህ ቀደም በተጻፈው መሰ ረት ምንም ውሳኔ እንዳልተሰጠ በሚመስል አይነት ይደረግ።

፳፰ ይህ በውጪ ያሉት የሊቀ ካህናት ሽንጎ የሚጠሩት በጣም [ሐ]አስቸጋሪ ለሆኑት የቤተክርስቲያን ጉዳዮች ነው፤ እና ምንም ተራ ወይም ልዩ ያልሆኑ ጉዳዮች እንደዚህ አይነት ሽንጎን ለመጥራት ብቁ አይደሉም።

፳፱ በውጪ የሚጓዙት እና የሚገኙት ሊቀ ካህናት እንደዚህ አይነት ሽንጎ ለመጥራት ወይም ላለመጥራት አስፈላጊ እንደሆነም ለመወሰን ሀይል አላቸው።

፴ በከፍተኛ ሽንጎ ወይም [መ]በሚጓዙ ሊቀ ካህናት እና የሚጓዙ የአስራ ሁለቱን [ሠ]ሐዋ ሪያት በያዘ ከፍተኛ ሽንጎ መካከል በውሳ ኔዎቻቸው ልዩነት አለ።

፴፩ ከመጀመሪያው ውሳኔ ይገባኝ ሊኖር ይችላል፤ ነገር ግን ከኋለኛው ውሳኔ ይግ ባኝ አይኖርም።

፴፪ የኋለኛው መጠራት የሚቻለው በቤ ተክርስቲያኗ አጠቃላይ ባለስልጣናት ብቻ፣ ይህም በመተላለፍ ጉዳይ ጊዜ ነው።

፴፫ ውሳኔ፥ የቤተክርስቲያኗ ቀዳሚ አመ ራር መቀመጫ ፕሬዘደንት ወይም ፕሬዘደ ንቶች ለይገባኝ ለመቅረብ የሚችል፣ እን ደዚህ አይነት ማንኛውም ጉዳይ፣ ይገባኙን እና ከእርሱ ጋር ያለውን መረጃና ምስክር ከመረመሩ በኋላ፣ ዳግም እንዲሰማ መብት እንደሚገባው ለመወሰን ሀይል አላቸው።

፴፬ አስራ ሁለቱ አማካሪዎች ከዚያም አስቀድሞ ማን እንደሚናገር ለመወሰን፣ እጣ ወይም መምረጫ ወረቀት ጣሉ፣ እና የሚቀጥለውም ውጤቱ ነበር፥ ፩፣ አሊቪር

[ሀ] ሀ ዘኍል. ፱፡፲፡ ፲፡
ለ ቅ.መ.መ. ራዕይ።

[ለ] ሀ ት. እና ቃ. ፪፲፯፡ ፫፲፡
[ሐ] ሀ ት. እና ቃ. ፪፲፯፡ ፳፫–፳፭፣

[መ] ሀ ት. ፳፡ ፲፡
[ሠ] ሐዋ ሪያ።

ካውድሪ፤ ፪፡ ጆሴፍ ኮ፤ ፫፡ ሳሙኤል ኤች ስሚዝ፤ ፬፡ ሉክ ጆንሰን፤ ፭፡ ጆን ኤስ ካርተር፤ ፮፡ ስይልቨስተር ስሚዝ፤ ፯፡ ጆን ጆንሰን፤ ፰፡ ኦርሰን ሀይድ፤ ፱፡ ጄርድ ካርተር፤ ፲፡ ጆሴፍ ስሚዝ፣ ቀዳማዊ፤ ፲፩፡ ጆን ስሚዝ፤ ፲፪፡ ማርቲን ሀሪስ።ከጸሎት በኋላ ጉባኤው ተበተነ።

ኦሊቨር ካውድሪ፣
ኦርሰን ሀይድ፣
ጸሀፊዎች

ክፍል ፲፫

በየካቲት ፳፬፣ ፲፰፻፴፭ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ ኦሀዮ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ይህ ራዕይ ፓርሊ ፒ ፕራት እና ላይመን ዋይት ስለእርዳታ እና በጃክሰን የግዛት ክፍል ውስጥ ወደሚገኘው መሬታቸው ቅዱሳንን ስለመመለስ ከነቢዩ ጋር ለመመካከር ከሚዙሪ ወደ ከርትላንድ ከደረሱ በኋላ የተቀበሉት ነበር።

፩–፬፣ ለምን ጌታ የጃክሰን የግዛት ክፍል ቅዱሳን እንዲሰደዱ እንደፈቀደ፤ ፭–፲፣ ትእዛዛትን ከጠበቁ ቅዱሳን ያሸንፋሉ፤ ፲፩–፳፣ የፅዮን ቤዛነት በሀይል ይመጣል፣ ጌታም በህዝቦቹ ፊት ይሄዳል፤ ፳፩–፳፰፣ ቅዱሳን በፅዮን ይሰብሰቡ፣ እና ሀይወታቸውን የሚያጡትም ደግመው ያገኙታል፤ ፳፱–፴፣ የተለያዩ ወንድሞች የፅዮንን ሰፈር እንዲያደራጁና ወደ ፅዮን እንዲሄዱ ተጠሩ፤ ታማኝ ከሆኑም ውጤታማ እንደሚሆኑ የተሰፋ ቃል ተሰጥቷቸዋል።

፩ ባልንጀሮቼ፣ እውነት እላችኋለሁ፣ እነሆ፣ በፅዮን ምድር የተበተኑትን ወንድሞቻችሁን ደህንነት እና [ሀ]ቤዛነት በሚመለከት ያላችሁን ሀላፊነት እንዴት [ለ]እንድት ፈፅሙ ታውቁ ዘንድ ራዕይና ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ፤

፪ ቁጣዬን በጊዜዬ ያለልክ በማወርድባቸው በጠላቶቼ እጆች [ሐ]እየተሰደዱ እና እየተመቱት ስላሉት።

፫ የጥፋታቸውንም መስፈሪያ [መ]ይሞሉ ዘንድ፣ ጽዋቸውም ሙሉ ይሆን ዘንድ፣ እስከአሁን ፈቅጄላቸዋለሁና፤

፬ እና በስሜ ራሳቸውን የሚጠሩትም ለጥቂት ዘመን በከፍተኛ እና አሳዛኝ ተግሳፅ [ሠ]ይገሰጹ ዘንድ፣ ምክንያቱም አብረውም የሰጠኋቸውን አስተሳሰብና ትእዛዛት [ረ]አላዳመጡምና።

፭ ነገር ግን እውነት እላችኋለሁ፣ እኔ ጌታ አምላካቸው የምሰጣቸውን [ሰ]ምክር ከዚህ ሰአት ጀምረው የሚያደምጡ ቢሆን፣ ህዝቤ ሊቀበሉ የሚችሉትን አዋጅ አውጃለሁ።

፮ እነሆ፣ ስላወጅኩት፣ ከዚህ ሰዓት ጀምሮ ጠላቶቼን ማሸነፍ ይጀምራሉ።

፯ እና እኔ ጌታ የምናገራቸውን ቃላት ለመከተል [ሸ]ቢያደምጡ፣ የአለም [ቀ]መን ግስታት ከእግሮቼ በታች እስከሚገዙ እና ምድርንም ለዘለአለም [በ]የራሳቸው እንዲያደርጓት [ተ]ለቅዱሳን [ቸ]እስከምትሰጥ ድረስ ማሸነፍን አያቆሙም።

፰ ነገር ግን ትእዛዛቴን [ኀ]እስካላከበሩ እና ቃላቴንም እስካልተከተሉ ድረስ፣ የአለም መንግስታት ያሸንፏቸዋል።

፲፫ ፩ *ሀ* ት. እና ቃ. ፲፩፡ ፴፫–፴፭።
ለ ት. እና ቃ. ፴፫፡ ፴።
፪ *ሀ* ት. እና ቃ. ፲፩፡ ፩፣ ፲፱፡ ፴፯።
፫ *ሀ* አልማ ፲፬፡ ፲–፲፩፣ ፴፡ ፲፫።
፬ *ሀ* ት. እና ቃ. ፣ ፲፩፡ ፩።
ለ ት. እና ቃ. ፲፩፡ ፴፫፣ ፲፱፡ ፴–፴፩።
ቅ.መ.መ. ምክር (ስም)።
፮ *ሀ* ት. እና ቃ. ፴፩፡ ፴፬።
ቅ.መ.መ. ታዛዥነት፣ ታዛዥ፣ መታዘዝ።
ለ ዳን. ፪፡ ፴፬።
ሐ ት. እና ቃ. ፴፯፡ ፴።
መ ቅ.መ.መ. ቅዱሳን።
ሠ ዳን. ፯፡ ፳፯።
፰ *ሀ* ሞዛያ ፩፡ ፲፫፣ ት. እና ቃ. ፹፪፡ ፲።

፱ ለአለም [ሀ]ብርሀንና ለሰዎች አዳኝ ይሆኑ ዘንድ ተመርጠው ነበርና፤

፲ እና የሰዎች አዳኞች እስካልሆናችሁ ድረስ፣ ጣዕሙን እንዳጣ [ሀ]ጨው ትሆናላችሁ፣ እና ከዚያን ጊዜ በኋላ ከንቱ ትሆናላችሁ፣ ደግሞም ትጣላላችሁ፣ እናም በሰዎችም እግር ትረገጣላችሁ።

፲፩ ነገር ግን እውነት እላችኋለሁ፣ የተበተኑት ወንድሞቻችሁ ወደ ውርስ [ሀ]መሬታቸው እንዲመለሱ፣ እና የፈረሱትን የፅዮን ስፍራዎችንም እንዲገነቡ አውጃለሁ።

፲፪ [ሀ]ከብዙ ስቃይ በኋላ፣ አስቀድሜ እንዳዘዝኳችሁ፣ በረከት ይመጣል።

፲፫ እነሆ፣ ይህም ከስቃያችሁ እና ከወንድሞቻችሁ ስቃይ በኋላ በተስፋ ቃል የሰጠኋችሁ በረከት ነው—ቤዛነታችሁ፣ እና የወንድሞቻችሁ ቤዛነት፣ እንዲሁም የፅዮን ምድር እንደገና እንዳትሸነፍ እንድትመሰረት ዳግም መመለሷ።

፲፬ ይህም ቢሆን፣ ውርሶቻቸውን ካረከሱ ይሸነፋሉ፤ ውርሶቻቸውን የሚያረክሱ ቢሆን አላድናቸውምና።

፲፭ እነሆ እላችኋለሁ፣ የፅዮን ቤዛነት በሀይል ይመጣ ዘንድ ይገባል፤

፲፮ ስለዚህ፣ [ሀ]ሙሴ የእስራኤልን ልጆች እንደመራው፣ የሚመራቸው ሰው ለህዝቤ አስነሳለሁ።

፲፯ እናንተ የእስራኤል ልጆች፣ [ሀ]የአብርሐም ዘር ናችሁና፣ እና በሀይሌና በተዘረጋው ክንዴ ከባርነታችሁ ተመርታችሁ መውጣት ያስፈልጋችኋልና።

፲፰ እና አባቶቻችሁ በመጀመሪያ እንደተመሩት፣ የፅዮን ቤዛነትም እንዲሁ ይሆናል።

፲፱ ስለዚህ፣ ልባችሁ አይታወክ፣ ለአባቶቻችሁ እንዳልኳቸው ለእናንተም እላችኋለሁና፥ በፊታችሁ [ሀ]መልአኬን እልካለሁ፣ ነገር ግን [ለ]እኔ በመካከላችሁ አልገለጥም።

፳ ነገር ግን እላችኋለሁ፥ በፊታችሁ [ሀ]መላዕክቴን እልካለሁ፣ እና በመካከላችሁም እገኛለሁ፣ እና በጊዜም መልካሙን ምድር [ለ]የራሳችሁ ታደርጋላችሁ።

፳፩ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ በሰጠኋችሁ ምሳሌ ውስጥ [ሀ]የወይን ስፍራው ጌታ የሆነው አገልጋይ የተናገረውን የሚመስለው [ለ]ሰው አገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ ነው።

፳፪ ስለዚህ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ ለቤቴ [ሀ]ጥንካሬ፣ ለወጣቶቼና ለጎልማሳዎቼ እንዲህ ይበል—በፅዮን ምድር፣ ለእኔ በተቀደሰው ገንዘብ በገዛሁት ምድር ላይ በአንድነት ተሰብሰቡ።

፳፫ እና ቤተክርስቲያኖቼ ሁሉ ብልህ ሰዎቻቸውን ከገንዘቦቻቸው ጋር ይላኩ፣ እና እንዳዘዝኩትም መሬቶችን [ሀ]ግዙ።

፳፬ እና የፅዮን ምድር እንዲሆን ከቀደስኩት [ሀ]ምድር፣ ከመልካሙ መሬቴ፣ እንዲሁም በእነርሱ ላይ በፊቴ ካመጣችሁት ከእነዚህ ምስክሮች በኋላ ከመሬታችሁ ሊያሰድዳችሁ ጠላቶቼ ከመጡባችሁ፣ እርገሟቸው፤

፳፭ እና ማንኛውም የምትረግሟቸውን፣ እረግማቸዋለሁ፣ እና ጠላቶቼንም ትበቀላላችሁ።

፳፮ እና በጠላቶቼ፣ በሚጠሉኝ ሶስተኛ እና አራተኛ ትውልድ ላይ [ሀ]ስትፈርዱም ከእናንተ ጋር እገኛለሁ።

፳፯ ለእኔ ህይወቱን ለመስጠት ማንም

፱ ሀ ፩ ኔፊ ፳፩፥፮።
፲ ሀ ማቴ. ፭፥፲፫–፲፮፤
ት. እና ቃ. ፻፩፥፴፱–፵።
፲፩ ሀ ት. እና ቃ. ፻፩፥፲፰።
፲፪ ሀ ራዕ. ፯፥፲፫–፲፬፤
ት. እና ቃ. ፶፰፥፬፤
፻፲፪፥፲፫።
፲፮ ሀ ዘፀአ. ፫፥፪–፲፤
ት. እና ቃ. ፻፯፥፺፩–፺፪።
ቅ.መ.መ. ሙሴ።
፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. አብርሐም—
የአብርሐም ዘር፤
የአብርሐም ቃል ኪዳን።
፲፱ ሀ ቅ.መ.መ. መላእክት።
ለ ት. እና ቃ. ፹፬፥፲፰–፳፬።
፳ ሀ ዘፀአ. ፲፬፥፲፱–፳።
ለ ት. እና ቃ. ፲፥፲፫።
፳፩ ሀ ቅ.መ.መ. የጌታ የወይን
አትክልት ስፍራ።
ለ ት. እና ቃ. ፻፩፥፶፭–፶፰።
፳፪ ሀ ት. እና ቃ. ፴፭፥፲፫–፲፬፤
፻፭፥፲፮፣ ፳፱–፴።
፳፫ ሀ ት. እና ቃ. ፵፪፥፴፭–፴፮፤
፶፯፥፭–፯፤ ፶፰፥፵፱–፶፩፤
፻፩፥፷፰–፸፬።
፳፬ ሀ ት. እና ቃ. ፳፱፥፯–፰፤
፵፭፥፳፬–፳፮፤ ፶፯፥፩–፪።
፳፮ ሀ ት. እና ቃ. ፺፯፥፳፪።

ሰው አይፍራ፤ ማንም ለእኔ ህይወቱን "አሳ ልፎ የሚሰጥ ዳግም ያገኘዋልና።

፳፯ እና ለእኔ ህይወቱን ለመስጠት ፈቃ ደኛ ያልሆነውም ደቀመዝሙሬ አይደለም።

፳፰ አገልጋዬ "ስድኒ ሪግደን፣ ቤተክር ስቲያኖችን ስለፅዮን ዳግም መመለስ እና ቤዛነት የሰጠኋቸውን ትእዛዛት እንዲጠብቁ ለማዘጋጀት፣ ለምስራቅ ሀገሮች ተሰብሳቢ ዎች ድምጹን ከፍ ማድረጉ ፍቃዴ ነው።

፳ አገልጋዬ "ፓርሊ ፒ ፕራትና አገልጋዬ ላይመን ዋይት፣ ወደፅዮን ምድር የሚሄዱ ሰዎችን በአስሮች ወይም በሀያዎች ወይም በሀምሳዎች ወይም በመቶዎች እስኪያደ ራጁ ድረስ፣ ለቤቴ ^ጥንካሬ አምስት መቶ ዎችን እስኪያገኙ ድረስ፣ ወደወንድሞቻ ቸው መሬት እንዳይመለሱ ፍቃዴ ነው።

፳፩ እነሆ ይህም ፍቃዴ ነው፤ ጠይቁ፣ ይሰጣችኋል፤ ነገር ግን ሰዎች ፈቃዴዬን ሁልጊዜም "አያደርጉም።

፳፪ ስለዚህ፣ አምስት መቶ የማታገኙ ቢሆን፣ ምናልባት ሶስት መቶ ታገኙ ዘንድ በቅንነት ፈልጉ።

፳፫ እና ሶስት መቶ ለማግኘት ባትች ሉም፣ ምናልባት አንድ መቶ ታገኙ ዘንድ በቅንነት ፈልጉ።

፳፬ ነገር ግን እውነት እላችኋለሁ፣ ወደ ፅዮን ምድር አብሮአችሁ እንዲሄዱ ከቤቴ ጥንካሬ መቶ እስክታገኙ ድረስ ወደፅዮን ምድር እንዳትሄዱ ትእዛዝን እሰጣችኋለሁ።

፳፭ ስለዚህ፣ እንዳልኳችሁ ጠይቁ፣ ይሰ ጣችኋል፤ አገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ ምናልባት ከእናንተ ጋር እንዲሄድ፣ እና በህዝቤ መካከል እንዲመራ፣ እና "በተ ቀደሰው ምድርም መንግስቴን ያደራጅ፣ እና የፅዮን ልጆችን በተሰጡት እና ወደፊት በሚሰጣችሁ ህግጋት እና ትእዛዛት መሰረት ይመሠርት ዘንድ በቅንነት ጸልዩ።

፳፮ ድልና ክብር ሁሉ የሚመጣላችሁ "በቅንነታችሁ፣ በታማኝነታችሁ፣ እና ^በእምነት ጸሎታችሁ ነው።

፳፯ አገልጋዬ ፓርሊ ፒ ፕራት ከአገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ ጋር ይጓዝ።

፳፰ አገልጋዬ ላይመን ዋይት ከአገልጋዬ ስድኒ ሪግደን ጋር ይጓዝ።

፳፱ አገልጋዬ ሀይረም ስሚዝ ከአገልጋዬ ፍሬድሪክ ጂ ዊሊያምስ ጋር ይጓዝ።

፴ አገልጋዬ ኦርሰን ሀይድ ከአገልጋዬ ኦርሰን ፕራት ጋር፣ አገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ በሚመክራቸው በማንኛውም፣ የሰጠኋቸውን የእነዚህን ትእዛዛት ፍጻሜ ያገኙ፣ ይጓዙ፣ እና የሚቀረውንም በእ ጆቼ ይተዉት። እንዲህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፲፬

በሚያዝያ ፳፫፣ ፲፰፻፳፭ (እ.አ.አ.)፣ በከርትላንድ፣ ኦሀዮ ወይም አካባቢ ስለት ብብር ድርጅት በሚመለከት ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተሰጠ ራዕይ (የክፍል ፫፰ እና ፱፪ ርዕሶችን ተመልከቱ)። ጊዜውም ምናልባት የትብብር ድርጅት አባላት በምክር ስብሰባ ቤተክርስቲያኗ ወዲያው ስለሚያስፈልጋት ለመወያየት በተሰበ ሰቡበት ጊዜ እንደነበር ይገመታል። ከዚህ በፊት በሚያዝያ ፲ በነበረው የድርጅቱ ስብሰባ ድርጅቱ እንዲፈርስ ተወስኖ ነበር። ይህ ራዕይ በምትኩ ይህ ድርጅት እን ደገና እንዲደራጅ መመሪያ ሰጠ፤ የዚህ ንብረቶችም ለድርጅቱ አባላት በመጋቢ

፳፯ ሀ ማቴ. ፲፡ ፴፱፤ ሉቃ. ፱፡ ፳፬፤ ት.እና ቃ. ፣፲፡ ፲፫–፲፭፤ ፲፳፬፡ ፲፱።

፳፰ ሀ ቅ.መ. ሪግደን፣ ስድኒ።

፳ ሀ ቅ.መ. ፕራት፣ ፓርሊ. ፓርከር።

ለ ት.እና ቃ. ፲፭፡ ፲፯።

፳፩ ሀ ት.እና ቃ. ፲፡ ፲።

፳፫ ሀ ት.እና ቃ. ፲፡ ፴፡ ፴፭።

፳፭ ሀ ቅ.መ.ት.ጋት።

ለ ት.እና ቃ. ፲፡ ፫፡ ፲፡ ፲፱–፲፡ ፲፱።

ነት ተከፋፍሎ ነበር። በጆሴፍ ስሚዝ አመራር ስር፣ “የትብብር ድርጅት” የሚባ ለው ሀረግ በኋላም በራዕዩ ውስጥ በ“የትብብር ስርዓት” ተተክቶ ነበር።

፩–፲፣ የትብብር ስርዓቱን የሚተላለፉት ቅዱሳን ይረገማሉ፤ ፲፩–፲፭፣ ጌታ ለቅ ዱሳኑን በራሱ መንገድ ያስተዳድራል፤ ፲፮–፲፰፣ የወንጌል ህግ ድሀን ስለመንከ ባከብ ይወስናል፤ ፲፱–፳፮፣ ለተለያዩ ወን ድሞች መጋቢነቶች እና በረከቶች ተመ ድበዋል፤ ፳፯–፳፱፣ በከርትላንድ ውስጥ ያለው የትብብር ስርዓት እና በፅዮን ያለው ስርዓት ተለያይተው ይሰሩ፤ ፳፱–፴፭፣ የጌታ ቅዱስ ሀብት ቅዱሳን መጻህፍትን ለማተም የተቋቋመ ነው፤ ፴፮–፴፯፣ የት ብብር ስርዓትአጠቃላይ ሀብት በጋራ ስም ምነት መሰረት ይሰራ፤ ፴፰–፴፱፣ በት ብብር ስርዓት ውስጥ ያሉት እዳዎቻቸውን ሁሉ ይክፈሉ፣ እና ጌታ ከገንዘብ እጦት ያድናቸዋል።

፩ ባልንጀሮቼ እውነት እላችኋለሁ፣ [1]የት ብብር ስርዓት እና ለቤተክርስቲያኔ ጥቅምና እስከምመጣም ድረስ ለሰዎች ደህንነት እን ዲሁም ዘለአለማዊ ስርዓትም ይሆን ዘንድ፣ እንዲደራጅ እና እንዲመሰረት ያዘዝኩት ንብረቶችን ስለሚመለከት ስርዓት ምክርና ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ—

፪ ያዘዝኳቸው ታማኝ ቢሆኑ በሚበዙ በረ ከቶች እንዲሁም በማይለወጥ እና በማይቀ የር ቃል ኪዳን ይባረካሉ፤

፫ ታማኝ እስካልሆኑ ድረስ ግን ለመረ ገም ይቀርባሉ።

፬ ስለዚህ፣ አንዳንድ አገልጋዮቼ ትእዛ ዜን እስካልጠበቁ ድረስ፣ [2]በመጎምጀት እና በሀሰት ቃላት ቃል ኪዳንን ከሰበሩ ግን፣ በከፍተኛ እና አሳዛኝ እርግማን እረግማ ቸዋለሁ።

፭ እኔ ጌታ በልቤ አውጀዋለሁና፣ ማንም ሰው በስርዓቱ አባል ሆኖ እየተላለፈ ቢገኘ፣ ወይም በሌላ ቃላት፣ የተሳሰራችሁበትን ቃል ኪዳን ብትሰብሩ፣ በዚህ ህይወት የረ ገማል፣ እና በምፈልገውም ከእግር ስር ይረ ገጣል።

፮ እኔ ጌታ በእነዚህ ነገሮች [3]አልዘበት ምና—

፯ እና ይህም ሁሉ በመካከላችሁ ያሉት ንጹሕ ትክክለኛ ካልሆኑት ጋር እንዳይ ኮነኑ ዘንድ ነው፤ እና በመካከላችሁ ያሉት ጥፋተኞችም እንዳያመልጡ፤ ምክንያ ቱም እኔ ጌታ በቀኝ እጄ በኩል ለእናንተ የክብር [4]አክሊል ቃል ኪዳን ገብቼአለ ሁና።

፰ ስለዚህ፣ እንደተላላፊ እስከተገኛችሁ ድረስ፣ ቁጣዬን በህይወታችሁ አታመል ጡም።

፱ በመተላለፍ [5]እስከተቆረጣችሁ ድረስ፣ እስከቤዛም ቀን ድረስ [6]የሰይጣንን [7]መን ገላታቶችን አያመልጡም።

፲ አሁንም ከመካከላችሁ ስርዓቱን ማንም ሰው ተላላፊ ሆኖ እና ለክፋቱ ንስሀ የም ይገባ ሆኖ ቢገኝ፣ ለሰይጣን መንገላታት አልፋችሁ እንድትሰጡ ዘንድ ከዚህ ሰዓት ጀምሮ ሀይልን እሰጣችኋለሁ፤ እና በእና ንተም ላይ ክፋትን [8]ያደርግ ዘንድ ሀይል አይኖረውም።

፲፩ ይህም በእኔ ዘንድ ጥበብ ነው፤ ስለ ዚህ፣ ራሳችሁን እንድታደራጁ እና ለእያን ዳንዱም ሰው [9]መጋቢነቱን እንድትመድቡ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ፤

፲፪ እያንዳንዱም ሰው ለተመደበበት መጋቢነት መልስ ይሰጠኝ ዘንድ ይሁን።

፲፫ እኔ ጌታ እያንዳንዱ ሰው ለፍጥረቶቼ ለሰራሁት እና ላዘጋጀሁት የምድር በረከ

---

[1] ፲፬ ፩ሀ ት. እና ቃ. ፴፯፡ ፫–፲፭። ቅ.መ.መ. የትብብር ስርዓት።
[2] ፩ሀ ቅ.መ.መ. መመኘት።
[3] ፮ሀ ገላ. ፮፡ ፯–፱።
[4] ፯ ሀ ኢሳ. ፷፪፡ ፫፣ ት. እና ቃ. ፵፯፡ ፲–፲፭። ቅ.መ.መ. ክብር።
[5] ፱ ሀ ቅ.መ.መ. ውግዘት። ለ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
[6] ሐ ት. እና ቃ. ፹፱፡ ፷፩። [7] ፲ ሀ ት. እና ቃ. ፲፱፡ ፷፫–፷፮። [8] ፲፩ ሀ ት. እና ቃ. ፵፪፡ ፷፭። ቅ.መ.መ. መጋቢ፣ መጋቢነት።

ቶች ᵐበመጋቢነት ᵃተጠያቂ ይሆንም ዘንድ ፍቃዴ ነውና።

፲፬ እኔ ጌታ የእውነት ᵐየእጄን ስራ ሰማያ ትን ዘረጋሁ፣ እና ምድርንም ᵃመሰረትሁ፤ እና በዚህ ያሉት ነገሮች ሁሉ የእኔ ናቸው።

፲፭ እና ቅዱሳኔን ማስተዳደር አላማዬ ነው፣ ሁሉም ነገሮች የእኔ ናቸውና።

፲፮ ነገር ግን፣ ይህም በእኔ ᵐመንገድ መደ ረግ አለበት፤ እና እነሆ እኔ ጌታ ቅዱሳኔን ለማስተዳደር፣ ᵃድሀዎቹን ከፍ ከፍ ለማ ድረግ፣ በዚያም ሀብታሞችንም ለማውረድ ይህን መንገድ አውጃለሁ።

፲፯ ᵐምድር ሙሉ ናት፣ እና በቂና የሚተ ርፍም አለና፤ አዎን፣ ሁሉንም ነገሮች አዘ ጋጅቻለሁ፣ እና ለሰዎች ልጆችም ለራሳ ቸው ᵃወኪል ይሆን ዘንድ ሰጥቻቸዋለሁ።

፲፰ ስለዚህ፣ ማንም ሰው እኔ ከሰራ ሁት ᵐየበዛውን ቢወስድ፣ እና በወን ጌሌ ᵃህግ መሰረት ᶜለድህውና ለችግረ ኛው ድርሻውን ባያካፍል፣ በስቃይ ውስጥ አይኑን ᵐበገሀነም ከክፉዎች ጋር ከፍ ያደርጋል።

፲፱ አሁንም ᵐስለስርዓቱ ንብረቶች እው ነት እላችኋለሁ—

፳ አገልጋዬ ስድኒ ሪግደን አሁን የሚኖር በት ስፍራና የቆዳ ፋብሪካ መሬት ለመጋቢ ነቱ፣ እና እኔ እንደ ፈቃዴ፣ እርሱን በማ ዝበት ጊዜ በወይን ስፍራ ሲያገለግል ይደ ገፍበት ዘንድ ይመደብለት።

፳፩ እና ሁሉም ነገር በከርትላንድ ምድር ውስጥ በሚኖረው በስርዓቱ ሽንጎ፣ እና በጋራ ስምምነት ወይም በስርዓቱ ድምፅ መሰረት ይደረግ።

፳፪ እና ይህን መጋቢነት እና በረከት እኔ ጌታ በአገልጋዬ ስድኒ ሪግደን ላይ ለእርሱ እና ከእርሱ በኋላ ለሚመጣው ዘሩ በረከት ይሆን ዘንድ እሰጠዋለሁ።

፳፫ እና በፊቴ ትሁት እስከሆነ ድረስ በረ ከቶችንም አበዛለታለሁ።

፳፬ ደግሞም፣ አገልጋዬ ጆን ጆንሰን በቀ ድሞው ውርሱ አማካይነት በቅያሬ ያገኘ ውን መሬት ለመጋቢነቱ አገልጋዬ ማርቲን ሀሪስ፣ ለእርሱ እና ከእርሱ በኋላ ላለው ዘሩ፣ ይመድብለት፤

፳፭ ታማኝ እስከሆነ ድረስ፣ በረከቶችንም ለእርሱ እና ከእርሱም በኋላ ላለው ዘሩ አበ ዛለታለሁ።

፳፮ እና አገልጋዬ ማርቲን ሀሪስ፣ አገል ጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ እንደመራው መሰረት፣ ገንዘቡን ቃላቴን ለማወጅ ያው ለው።

፳፯ ደግሞም፣ አገልጋዬ ፍረድሪክ ጂ ዊሊያምስ አሁን የሚኖርበት አካባቢ ስፍራ ይሰጠው።

፳፰ እና አገልጋዬ ኦሊቨር ካውድሪ ለእት መት ቢሮ ይሆነው ዘንድ፣ ቁጥር አንድ የሆነ የመሬት፣ ከቤቱ አጠገብ ባለው መሬት፣ ደግሞም አባቱ በሚኖርበት ስፍራ መሬት ይሰጠው።

፳፱ እና አገልጋዮቼ ፍረድሪክ ጂ ዊሊያ ምስ እና ኦሊቨር ካውድሪ የእትመት ቢሮ ከሁሉም ነገሮቼ ጋር ይሰጣቸው።

፴ እና ይህም ለእነርሱ የሚመደብላቸው መጋቢነት ይሆናል።

፴፩ እና ታማኝም እስከሆኑ ድረስ፣ እነሆ እባርካቸዋለሁ፣ እና በረከቶቻቸውንም አባዛላቸዋለሁ።

፴፪ ይህም ለእነርሱ እና ከእነርሱ በኋላ ለሚመጡ ዘሮቻቸው የመደብኩላቸው መጋቢነት መጀመሪያ ነው።

፲፫ *ሀ* ት. እና ቃ. ፳፪፡ ፫–፭፣ ፲፯–፳፪።
ለ ቅ.መ.መ. መልስ መስጠት፣ ሂሳብ፣ ተጠያቂነት፣ ሀላፊነት።
፲፬ *ሀ* መዝ. ፲፱፡ ፩፣ ፳፬፡ ፩።
ለ ኢሳ. ፵፪፡ ፭፣ ፵፭፡ ፲፪።
ቅ.መ.መ. መፍጠር፣ ፍጥረት።
፲፭ *ሀ* ት. እና ቃ. ፲፭፡ ፭።
ቅ.መ.መ. በጎ ድርጊት።
ለ ፩ ሳሙ. ፪፡ ፯–፰፣ ሉቃ. ፩፡ ፶፭–፶፣ ት. እና ቃ. ፲፰፡ ፲፯።
፲፯ *ሀ* ት. እና ቃ. ፶፱፡ ፲፯–፳።
ቅ.መ.መ. ምድር።
ለ ቅ.መ.መ. ነጻ ምርጫ።
፲፰ *ሀ* ሉቃ. ፲፡ ፲፩፣ ያዕ. ፪፡ ፲፭–፲፯።
ለ ት. እና ቃ. ፵፪፡ ፴።
ሐ ምሳ. ፲፡ ፳፩፣ ሞዛያ ፩፡ ፳፯፣ ት. እና ቃ. ፶፪፡ ፵።
መ ሉቃ. ፲፯፡ ፳–፴፩።
፲፱ *ሀ* ቅ.መ.መ. የትብብር ስርዓት።

፴፫ እና፣ ታማኝ እስከሆኑ ድረስ፣ ለእነ ርሱ እና ከእነርሱ በኋላ ለዘሮቻቸው በረከ ቶችን፣ እንዲሁም ብዙ በረከቶችን፣ አበ ዛላቸዋለሁ።

፴፬ ደግሞም፣ አገልጋዬ ጆን ጆንሰን በው ርሱ ያሉትን ቤቶቼን ᐧᐧለመገንባት ከተመደ በው ምድር እና ለአገልጋዬ ኦሊቨር ካው ድሪ ከተመደበው በስተቀር ሁሉም የሚኖ ርበት ቤትና ውርስ ይሰጠው።

፴፭ እና ታማኝ እስከሆነ ድረስ፣ በረከቶ ችን አበዛለታለሁ።

፴፮ እና በመንፈስ ᐧᐧድምፅ እንዲያውቅ እስከተደረገለት ድረስ፣ እና በስርዓቴ ምክር መሰረት፣ እና በስርዓቴ ድምፅ የቅዱሳኔን ከተማ ለመገንባት የተቀመጡትን መሬቶች ይሸጥም ዘንድ ፍቃዴ ነው።

፴፯ ይህም ለእርሱ እና ከእርሱ በኋላ ለዘሩ ለበረከት የመደብኩት የመጋቢነት መጀመ ሪያ ነው።

፴፰ እና ታማኝ እስከሆነም ድረስ የበረከ ቶች ብዛት አበዛለታለሁ።

፴፱ ደግሞም፣ ለአገልጋዬ ᐧᐧኒውል ኬ ዊትኒ አሁን የሚኖርበት ቤት እና መሬት፣ እና ግብይት ከሚገኝበት መሬት እና ህንጻ፣ እና ከግብይቱ ስፍራ በስተደቡብ ያለው መሬት፣ እና ደግሞም ፖታሽ የሚሰራበት ምድር ይመደብለት።

፴ እና ይህን ሁሉ ለአገልጋዬ ኒውል ኬ ዊትኒ ለመጋቢነት የመደብኩት ለእርሱ እና ከእርሱ በኋላ ለዘሩ በረከት፣ በከርትላ ንድ ምድር ውስጥ ለስቴኬ ለመሰረትኩት ግብይት ይሆን ዘንድ ነው።

፴፩ አዎን፣ በእውነት ይህም፣ እንዲሁም የግብይይቱ ስፍራ ሁሉ፣ ለአገልጋዬ ኤን ኬ ዊትኒ፣ ለእርሱና ᐧᐧለወኪሉ እና ከእርሱም በኋላ ለዘሩ የመደብኩት መጋቢነት ነው።

፴፪ እና የሰጠሁት ትእዛዛቴን ለመጠበቅ ታማኝ እስከሆነ ድረስ፣ ለእነርሱ እና ከእ ነርሱ በኋላ ለዘሮቹ በረከቶችን፣ እንዲሁም የተትረፈረፉ በረከቶችን፣ አበዛላቸዋለሁ።

፴፫ ደግሞም፣ አገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ ለሁለት መቶ ሜትር ርዝመት እና ስልሳ ሜትር ስፋት ያለው ለቤቴ መገንቢያ ይሆን ዘንድ የተቀመጠው መሬት፣ ደግ ሞም አባቱ አሁን በሚኖርበት ውርስ ይመ ደብለት።

፴፬ ይህም ለእርሱ እና ከእርሱ በኋላ ለዘሩ፣ ለእርሱ እና ለአባቱ በረከት፣ የመ ደብኩለት መጋቢነት መጀመሪያ ነው።

፴፭ እነሆ፣ ᐧᐧአባቱ ይረዳበት ዘንድ ወር ስን አስቀምጫለሁና፤ ስለዚህ እንደአገል ጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ ቤት አባልም ይቆጠራል።

፴፮ እና በአገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ ታማኝ እስከሆነ ድረስ በቤቱ በረከቶችን፣ እንዲሁም የተትረፈረፉ በረከቶችን አበዛ ለታለሁ።

፴፯ አሁንም ስለፅዮን በሚመለከት ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ፣ እንደትብብር ስርዓት በፅዮን ካሉት ወንድሞቻችሁ ጋር፣ ከዚህ ጉዳይ በስተቀር፣ ከዚህ በኋላ እንዳትተሳሰሩ—

፴፰ ከተደራጃችሁ በኋላ፣ በከርትላንድ ከተማ ውስጥ የፅዮን ᐧᐧካስማ የትብብር ስር ዓት ተብላችሁ ትጠራላችሁ። እና ወንድሞ ቻችሁም፣ ከተደራጁ በኋላ፣ የፅዮን ከተማ የትብብር ስርዓት ተብለው ይጠራሉ።

፴፱ እና በራሳቸውም ስሞች፣ እና በራሳ ቸው ስምም ይደራጁ፤ እና የራሳቸውንም ጉዳይ በራሳቸው ስም፣ እና በራሳቸው ስሞ ችም፣ ያድርጉ፤

፴ እና የራሳችሁንም ስራ በስማችሁ፣ እና በስሞቻችሁም አድርጉ።

፴፩ እና ይህ እንዲደረግ የማዝዘው እነ ርሱ ᐧᐧበመሰደዳቸው እና ወደፊት ለሚመ ጣው ደህንነታችሁ፣ እና ለእነርሱም ደህ ንነት ነው።

፴፬ ᐧᐧ ት. እና ቃ. ፴፬፡፫፣ ፲፡ ፲፡
፴፯ ᐧᐧ ቅ.መ.መ. ራዕይ።
፴፱ ᐧᐧ ቅ.መ.መ. ዊትኒ፣ ኒውል ኬ።
፴፩ ᐧᐧ ት. እና ቃ. ፹፬፡ ፻፲፭–፻፲፮።

፴፭ ᐧᐧ ት. እና ቃ. ፶፡ ፳።
ቅ.መ.መ. ስሚዝ፣ ጆሴፍ ቀዳማዊ።
፴፮ ᐧᐧ ት. እና ቃ. ፹፪፡ ፲፫፣ ፶፬፡ ፩፣ ፻፲፡ ፻፲፱።
ቅ.መ.መ. ካስማ።
፴፩ ᐧᐧ ት. እና ቃ. ፻፲፱፡ ፴፯።

፶፪ በመተላለፍ፣ ᵐበመጎምጀት እና በሀሰት ᵃቃል በኩል ቃል ኪዳን ስለተሰ በረ—

፶፫ ስለዚህ፣ ከወንድሞቻችሁ ጋር የነበራ ችሁ የትብብር ስርዓት ፈርሷል፣ እና እንዳ ልኩት በዚህ መንገድ፣ ይህ ስርዓት፣ ሁኔ ታችሁ በሚፈቅደው እና በሸንጎው ቀጥ ተኛ ድምፅ፣ ከዚህ ሰዓት በኋላ ከእነርሱ ጋር የምትተሳሰሩት በሸንጎ በሚስማሙ በት ብድር ብቻ ነው።

፶፬ ደግሞም፣ የመደብኩላችሁን መጋቢ ነት በተመለከተ ትእዛዝን እሰጣችኋለሁ።

፶፭ እነሆ፣ እነዚህ ንብረቶች ሁሉ የእኔ ናቸው፣ አለበለዚያም እምነታችሁ በከንቱ ነው፣ እና እናንተም ግብዞች ናችሁ፣ እና ለእኔ የገባችሁትም ቃል ኪዳን ተሰብሯል፤

፶፮ እና ንብረቶቹ የእኔ ከሆኑ፣ እናንተም የእኔ ᵐመጋቢዎች ናችሁ፤ አለበለዚያ መጋ ቢዎች አይደላችሁም።

፶፯ ነገር ግን፣ እውነት እላችኋለሁ፣ በቤቴ ላይ መጋቢ፣ እንዲሁም በእርግጥም መጋ ቢዎች ትሆኑ ትሆኑ መድቤአችኋለሁ።

፶፰ እና ለዚህ አላማ ራሳችሁን እንድታ ደራጁ፣ እንዲሁም የቅዱስ መጻህፍቶቼን፣ የሰጠኋችሁን፣ ከዚህ በኋላም ከጊዜ ወደ ጊዜ የምሰጣችሁን ራዕዮች፣ እና ᵐየቃላቴን ሙላት እንድታትሙ አዝዤአችኋለሁ—

፶፱ ቤተክርስቲያኔን እና መንግስቴን በምድር ላይ ለመገንባት ባለኝ አላማ፣ እና ቅርብ ለሆነው፣ ህዝቤንም አብሬ ከእነርሱ ጋር ᵐለምኖርበት ᵃጊዜ አዘጋጃቸውም ዘንድ ነበር።

፷ እና ለራሳችሁም የግምጃ ቤት አዘጋጁ፣ እና በስሜም ቀድሱት።

፷፩ እና ከመካከላችሁ አንዱ የግምጃ ቤቱን እንዲጠብቅ መድቡ፣ እና ለዚህ በረከትም ይሾማል።

፷፪ እና በግምጃ ቤቱም ላይ ማህተም ይኖ ራል፣ እና ሁሉም ቅዱስ ነገሮች ወደ ግምጃ ቤት ይወሰዳሉ፤ እና ከመካከላችሁ ማንም ይህን፣ ወይም ማንኛውንም ክፍል፣ የራሴ ነው ብለው አይጠሩትም፣ ይህም በአንድ ስምምነት ለሁላችሁም ይሆናልና።

፷፫ ደግሞም ይህን ከዚህ ሰዓት ጀምሮ እሰጣችኋለሁ፤ እና ይህም እንዲደረግ አድ ርጉ፣ ሂዱ እና እንዳልኩት እነዚህን የተቀ ደሱ ነገሮችን ለማሳተም ለዚህም አላማ፣ ከቅዱሱ ነገሮች በስተቀር፣ የተመደበላች ሁን መጋቢነት ተጠቀሙበት።

፷፬ እና የቅዱስ ነገሮች ᵐትርፍም በግምጃ ቤት ውስጥ ይቀመጥ፣ እና ማህተሙም በዚህ ላይ ይሁን፤ እና በስርዓት ድምፅ ወይም በትእዛዝ ካልሆነ በስተቀር፣ በማ ንም ሰው ይህን ነገር አይጠቀምበት ወይም ከግምጃ ቤቱ አያውጡት፣ ወይም የታተ መበትም አይፈታ።

፷፭ እንደዚሁም የቅዱስ ነገሮችን ትርፍ፣ ለተቀደሰ እና ቅዱስ አላማ፣ በግምጃ ቤት ትጠብቃላችሁ።

፷፮ እና ይህም የጌታ የተቀደሰ ግምጃ ቤት ይባላል፤ እና ለጌታ ቅዱስ እና የተቀደሰ ይሆን ዘንድ ማህተምም ይታተማል።

፷፯ ደግሞም፣ ሌላ ግምጃ ቤት ይዘጋጅ፣ እና የንብረት ሀላፊ የግምጃ ቤትን እንዲ ጠብቅ ይመደብ፣ እና በዚህም ላይ ማህ ተም ይደረግ፤

፷፰ እና የመደብኩላችሁን ንብረቶች፣ በቤቶች፣ ወይም በመሬቶች፣ ወይም፣ ለቅዱስ እና ለተቀደሰ አላማ ከምጠብቃ ቸው ከቅዱስ እና ከተቀደሱ ፅህፈቶች በስ ተቀር በሁሉም ነገሮች በማሻሻል በመጋ ቢነታችሁ የተቀበላችሁት ገንዘብ በመቶ ዎች፣ ወይም በሀምሳዎች፣ ወይም በሀያ ዎች፣ ወይም በአስሮች፣ ወይም በአምስ ቶች ሁሉ ወደ ግምጃ ቤቱ ገንዘቡ ወዲያው እንደተቀበላችሁ አስገቡት።

፶፪ ᵐ ቅ.መ.መ. መመኘት።
ᵃ ቅ.መ.መ. ቃል ኪዳን።

፶፮ ᵐ ቅ.መ.መ. መጋቢ፣ መጋቢነት።

፶፯ ᵐ ቅ.መ.መ. የጆሴፍ ስሚዝ ትርጉም (ጆ.ስ.ት.)።

፶፱ ᵐ ት. እና ቃ. ፩፡ ፴፩–፴፮፤ ፷፭፡ ፱–፲፩።

ᵃ ቅ.መ.መ. አንድ ሺህ አመት።

፷፩ ᵐ ይህም ትርፎች ወይም በእጅ የገቡት ገንዘቦች ማለት ነው።

፳፱ ወይም በሌላ አባባል፣ ማንኛውም ሰው አምስት ብር ቢያገኝ ወደ ግምጃ ቤት ያስገባው፤ ወይም አስር፣ ወይም ሀያ፣ ወይም ሀምሳ፣ ወይም መቶ ቢያገኝ እን ዲሁ ያድርግ፤

፳ እና በመካከላችሁ ማንም ሰው የእኔ ነው የሚለው አይኑር፤ ይህ ወይም ማንኛውም ክፍል፣ የእርሱ ተብሎ አይጠራምና።

፳፩ እና በስርዓት ድምፅ እና በጋራ ስም ምነት ካልሆነ በስተቀር፣ ማንኛውንም ክፍል አይጠቀሙበት ወይም ምንም ነገር ከግምጃ ቤቱ አይውጣ።

፳፪ እና ይህም የስርዓት ድምፅ እና የጋራ ስምምነት ይሆናል—ከመካከላችሁ ማንም ሰው ለንብረት ሀላፊው እንዲህ ቢል፥ በመጋቢነቴ እንደረዳኝ ይህ ያስ ፈልገኛል—

፳፫ አምስት ብር፣ ወይም አስር ብር፣ ወይም ሀይ፣ ወይም ሀምሳ፣ ወይም መቶ ቢሆነ፣ የንብረት ሀለፊው በመጋቢነቱ እን ዲረዳው የሚያስፈልገውን ይሰጠዋል—

፳፬ ይህም በስርዓቱ ሽንጎ ፊት ታማኝ እን ዳልሆነ እና [a]ብልህ መጋቢ እንዳልሆነ በግ ልፅ እስከሚታይ ድረስ የሚያስፈልገው ይሰጠዋል።

፳፭ ነገር ግን ሁሉ አባል ከሆነ፣ እና በመ ጋቢነቱ ታማኝ እና ብልህ ቢሆን፣ ይህም ለንብረት ሀላፊው ምልክት ስለሚሆንለት ንብረት ሀላፊው አይከልከለው።

፳፮ ነገር ግን በመተላለፍ ምክንያት፣ የንብረት ሀላፊው ለሽንጎው እና ለስርዓቱ ድምፅ መላሽ ይሆናል።

፳፯ እና የንብረት ሀላፊው ታማኝ እና ብልህ መጋቢ ሆኖ በማይገኝበት ጉዳይ፣ ለሽንጎው እና ለስርዓቱ ድምፅ መላሽ ይሆ ናል፣ እና ከስፍራውም ይወጣል፣ እና በእ ርሱም ምትክ [b]ሌላ ይመደባል።

፳፰ ደግሞም፣ እዳዎቻችሁን በሚመለ ከት እውነት እላችኋለሁ—እነሆ [c]እዳዎ ቻችሁን ሁሉ [d]እንድትከፍሉ ፍቃዴ ነው።

፳፱ እና በፊቴም [e]ትሁት እንድትሆኑ፣ እና ይህን በረከት [f]በቅንነት እና በየዋህነትና በእምነት ጸሎታችሁ እንድታገኙ ፍቃዴ ነው።

፴ እና ቅን እና ትሁት እስከሆናችሁ እና የእምነት [g]ጸሎትን እስከተጠቀማችሁበት ድረስ፣ እነሆ የማድናችሁበት መንገድ እስ ከምልክላችሁ ድረስ፣ የአበዳሪዎቻችሁን ሰዎች ልብ አራራለሁ።

፴፩ ስለዚህ፣ ወደ ኒው ዮርክ ወዲያው ጻፉ እና [h]በመንፈሴ እንደተሰጣችሁም መሰረት ጻፉ፤ እና በእናንት ላይ ስቃይ ለማ ምጣት በአዕምሮአቸው ላይ ያለውን ይወ ሰድ ዘንድ የአበዳሮዎቻችሁን ልብ አራ ራለሁ።

፴፪ እና [i]ትሁት እና ታማኝ ብትሆኑ እና ስሜን የምትጠሩ እስከሆናችሁ ድረስ፣ እነሆ፣ [j]ድልን እሰጣችኋለሁ።

፴፫ ለዚህም አንዴ ከባርነታችሁ ትወጡ ዘንድ፣ የተሰፋ ቃልም እሰጣችኋለሁ።

፴፬ ገንዘብ በመቶዎች፣ ወይም በሺዎች፣ እንዲሁም ራሳችሁን ከእስር ለማውጣት መበደር እስከምትችሉት ድረስ ለማግኘት እድል እስካገኛችሁ ድረስ፣ ይህ መብታ ችሁ ነው።

፴፭ እና በእጆቻችሁ የሰጠኋችሁን ንብረ ቶችም፣ ለዚህ አንድ ጊዜ ስማችሁን በጋራ ስምምነት ወይም በሌላ በመስጠት፣ ወይም መልካም በሚመስላችሁ፣ በእዳ አስይዙ።

፴፮ ይህን ልዩ መብት ለአንድ ጊዜ እሰ ጣችኋለሁ፤ እነሆም፣ በፊታችሁ የዘረጋሁ ትን ነገሮች፣ በትእዛዛቴ መሰረት ለማድረግ ብትቀጥሉ፣ ሁሉም ነገሮች የእኔ ናቸው፣ እና እናንተም የእኔ መጋቢዎች ናችሁ፣ እና መምህር ቤቱ እንዲሰበር አይፈቅድምና። እንዲህም ይሁን። አሜን።

---

[a] ፳፬ ሀ ሉቃ. ፲፮፡ ፩–፲፪።
[b] ፳፯ ሀ ት. እና ቃ. ፲፯፡ ፶፱–፸።
[c] ፳፰ ሀ ቅ.መ.መ. እዳ።
ለ ት. እና ቃ. ፵፪፡ ፶፩።
[d] ፳፱ ሀ ቅ.መ.መ. ትሁት፣ ትሕትና።
ለ ቅ.መ.መ. ትጋት።
[e] ሀ ያዕ. ፭፡ ፲፭።
[f] ፴፩ ሀ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
[g] ፴፪ ሀ ሉቃ. ፲፡ ፲፩፤
ት. እና ቃ. ፳፯፡ ፲።
ለ ት. እና ቃ. ፲፫፡ ፴፯።

ክፍል ፲፭

በሰኔ ፳፪፣ ፲፰፻፴፭ (እ.አ.አ.) በሚዙሪ ፊሺንግ ወንዝ ላይ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። በነቢዩ አመራር ስር፣ ከኦሀዮ እና ሌሎች አካባቢዎች የመጡ ቅዱሳን በኋላ የፅዮን ሰፈር ተብሎ በሚታወቀው ጉዞ ወደ ምዙሪ ተሰ ልፈው ሄዱ። አላማቸውም ከምዙሪ በግድ የወጡትን ቅዱሳን አጅበው በጃክሰን የግዛት ክፍል ወደነበሩበት መሬታቸው ለመመለስ ነበር። ቅዱሳንን ያሳደዱ የም ዙሪ ሰዎች የፅዮን ሰፈር ጸያፍ እርምጃ ይወስዱብናል ብለው ፈርተው ነበር እናም በክሌይ የግዛት ክፍል፣ ምዙሪ ውስጥ የሚኖሩትን ቅዱሳን አስቀድመው አጥቅ ተው ነበር። የምዙሪ ገዢ ቅዱሳንን ለመርዳት የገባውን ቃል መልሶ ሲወስድ፣ ጆሴፍ ይህን ራዕይ ተቀበለ።

፩–፰፣ ፅዮን የምትገነባው የሰለስቲያል ህግን ጠባቂ በመሆን ነው፤ ፯–፲፫፣ የፅዮን ቤዛነት ለጥቂት ጊዜ ተላልፏል፣ ፲፬–፲፱፣ ጌታ የፅዮንን ጦርነት ይዋጋል፤ ፳–፳፯፣ ቅዱሳን ብልሆች ይሁኑ እና ሲሰበሰቡም በታላቅ ስራዎች ኩራት አይሰማቸው፤ ፳፰–፴፣ በጃክሰን እና በአጠገቡ የግዛት ክፍሎች መሬቶች ይገዙ፤ ፴፩–፴፴፣ ሽማ ግሌዎች በከርትላንድ ውስጥ በጌታ ቤት ውስጥ መንፈሳዊ ስጦታ ይቀበሉ፤ ፴፫–፴፯፣ የተጠሩት እና የተመረጡት ቅዱ ሳን ይቀደሳሉ፤ ፴፰–፴፱፣ ቅዱሳን ለአ ለም የሰላም አርማን ያንሱ።

፩ የተሰቃዩ ህዝቤን [a]ቤዛነት በሚመለከት ፈቃዴን ትማሩ ዘንድ ራሳችሁን ለሰበሰባ ችሁት እውነት እላለሁ—

፪ እነሆ፣ እላችኋለሁ፣ ስለግለሰብ ሳይ ሆን ስለቤተክርስቲያኗ ስናገር፣ በህዝቤ [b]መተላለፍ ባይሆን ኖሮ፣ አሁንም ይድኑ ነበር።

፫ ነገር ግን እነሆ፣ በእጆቻቸው ለምጠ ብቃቸው ነገሮች ታዛዥ ለመሆን አልተማ ሩም፣ ነገር ግን በክፋት የተሞሉ ናቸው፣ እና እቃዎቻቸውን በቅዱሳን እንደሚገ ባው ለድሆችና በመካከላቸው ለሚሰቃዩት [c]አያካፈሉም፤

፬ እና በሰለስቲያል መንግስት ህግ መሰ ረት አስፈላጊ በሆነው [d]ህብረትም አይተ ባበሩም፤

፭ እና [e]ፅዮን ካለሰለስቲያል መንግስት [f]ህግ መሰረታዊ መርሆች ካልሆነ [g]በስተ ቀር ልትገነባ አይቻላትም፤ አለበለዚያም ወደ ራሴ ልቀበላት አልችልም።

፮ እና ህዝቤ [h]ታዛዥነት እስኪማሩ ድረስ፣ አስፈላጊም ቢሆን በሚሰቃዩባቸው ነገሮች [i]መገሰፅ ያስፈልጋቸዋል።

፯ የምናገረው ህዝቤን እንዲመሩ ስለተመ ደቡት የቤተክርስቲያኔ [j]የመጀመሪያ ሽማ ግሌዎች አይደለም፣ ሁሉም በፍርድ ላይ አይደሉምና፤

፰ ነገር ግን በሌላ ስፍራ ስላሉት ቤተክር ስቲያኔ በሚመለከት እናገራለሁ—እንዲህ የሚሉ ብዙ አሉ፥ አምላካቸው የት አለ? እነሆ፣ በችግር ጊዜ ያድናቸዋል፣ አለበለ ዚያም ወደፅዮን አንሄድም፣ እና ገንዘባች ንንም እናስቀራለን።

፱ ስለዚህ፣ በህዝቤ [k]መተላለፍ ምክንያት ሽማግሌዎቼ የፅዮን ቤዛነት ለትንሽ ዘመን ይጠብቁ ዘንድ ፍቃዴ ነው—

፲፭ ፩ሀ ት.እና ቃ. ፲፡ ፲፫።
ፍ ሀ ት.እና ቃ. ፲፩፡ ፩–፰፣ ፶፪።
፫ ሀ የሐዋ. ፭፡ ፩–፲፩፣
ት.እና ቃ. ፶፪፡ ፴።
ቅ.መ.መ. መቀደስ፣
የቅድስና ህግ።
፬ ሀ ት.እና ቃ. ፸፯፡ ፫–፮።
፭ ሀ ቅ.መ.መ. ፅዮን።
ለ ት.እና ቃ. ፲፫፡ ፳፪።
ሐ ት.እና ቃ. ፲፩፡ ፲፭–፲፯።
፮ ሀ ቅ.መ.መ. ታዛዥነት፣
ታዛዥ፣ መታዘዝ።
ሰ ት.እና ቃ. ፯፡ ፲–፲፪።
ቅ.መ.መ. መገሰጽ፣ ተግሳጽ።
፯ ሀ ት.እና ቃ. ፳፡ ፪–፫።
፱ ሀ ት.እና ቃ. ፲፫፡ ፩።

፲ ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ፣ እና ህዝቤ በፍጹም እንዲማሩ፣ እና አጋጣሚም እን ዲያገኙ፣ እና ᵐሀላፊነታቸውንና ከእጆቻ ቸው የምፈልገውን ነገሮች በሚመለከት በፍጹም ይማሩ ዘንድ ነው።

፲፩ እና ᵐሽማግሌዎቼ ከላይ የኃይል ᵃመን ፈሳዊ ስጦታ እስኪሰጣቸው ድረስ ይህም ሆኖ አይሆንም።

፲፪ እነሆ፣ ታማኝ ቢሆኑ እና በፊቴም በት ህትና እስከቀጠሉ ድረስ፣ ታላቅ መንፈሳዊ ስጦታ እና በረከት በእነርሱ ላይ ᵐለማፍሰስ አዘጋጅቻለሁ።

፲፫ ስለዚህ ለፅዮን ቤዛነት ሽማግሌዎቼ ለጥቂት ዘመን ይጠብቁ ዘንድ ፍቃዴ ነው።

፲፬ እነሆ፣ የፅዮንን ጦርነት እንዲዋጉ በእጆቻቸው አልፈልግባቸውምና፤ ከዚህ በፊት ትእዛዝ እንደሰጠሁት፣ ይህንንም አሟላለሁና—ጦርነታችሁን ᵐእዋጋላችኋ ለሁ።

፲፭ እነሆ፣ ᵐአጥፊው ጠላቶቼን እንዲ ያጠፋ እና እንዲያባክን ልኬዋለሁ፤ እና ከብዙ አመታት በኋላ ውርሴን እንዲበ ክሉ፣ እና ለቅዱሳኔ መሰብሰብ ᵃበቀደስኩ ባቸው ምድሮች ላይ ስሜን ᵐእንዲሰድቡ አይተዉም።

፲፮ እነሆ፣ አገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግ ማዊ ለቤቴ ᵐጥንካሬ፣ እንዲሁም ጆግኖ ቼን፣ ወጣት ወንዶቼን፣ እና ጎልማሳዎቼን ለህዝቤ ቤዛነት እንዲሰበሰቡ፣ እና የጠላቶ ቼን ማማዎች እንዲጥሉ፣ እና ᵃጠባቂዎቻ ቸውንም እንዲበትኑ እንዲነግራቸው አዘ ዝኩት፤

፲፯ ነገር ግን የቤቴ ጥንካሬ ቃላቴን አላ ደመጡም።

፲፰ ነገር ግን ቃላቴን ያደመጡ እስካሉ ድረስ፣ በታማኝነት ቢቀጥሉ በረከት እና ᵐየመንፈስ ስጦታ አዘጋጅቼላቸዋለሁ።

፲፱ ጸሎታቸውን ሰምቻለሁ፣ እና ስለታ ቸውን እቀበላለሁ፤ እና ᵐእምነታቸውም ተፈትኖ እስከዚህ ድረስ ይመጡም ዘንድ ፍቃዴ ነው።

፳ አሁንም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ትእ ዛዝንም እሰጣችኋለሁ፣ ወደዚህ እስከመ ጣችሁ ድረስ በአካባቢው ለመቆየት የሚ ችሉ ይቆዩ፤

፳፩ መቆየት የማይችሉት፣ በምስራቅ ቤተሰብ ያላቸውም፣ አገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ፣ ዳግማዊ፣ እስከመደባቸው ድረስ ለትንሽ ዘመን ይቆዩ፤

፳፪ ስለዚህ ጉዳይ እመክረዋለሁ፣ እና ለእነርሱ የሚመደቡላቸው ማናቸውም ነገ ሮች ሁሉ ይሟላሉ።

፳፫ እና በዚህ አካባቢ የሚኖሩት ህዝቤ ሁሉ ታማኝ እና ጸሎተኛ እና በፊቴ ትሁት ይሁኑ፣ እና የገለጥኩላቸውን ነገሮችንም እንዲገልጹ በእኔ ዘንድ ጥበብ እስኪሆን ድረስ አይግለጿቸው።

፳፬ ስለፍርድም አትናገሩ፣ ስለእምነት ወይም ስለታላቅ ስራም ᵐኩራት አይሰማ ችሁ፣ ነገር ግን በምትችሉት መጠን በአ ንድ አካባቢ፣ ለሰዎች ስሜት እያሰባችሁ በጥንቃቄ ተሰብሰቡ።

፳፭ እነሆም፣ ᵐበሰላም እና በደህንነት ታርፉ ዘንድ፣ ለህዝቦቹም፥ ፍርድ እና ጽድቅን በህጉ መሰረት ፈፅሙ፣ እና በደላ ችንን መልሱልን እያላችሁ፣ በአይኖቻቸው ውስጥም ውለታ እና ጸጋ እሰጣችኋለሁ።

፳፮ እነሆ፣ ባልንጀሮቼ አሁን እላች ኋለሁ፣ በዚህም መንገድ፣ የእስራኤል ᵐሰራዊት እጅግ ታላቅ እስኪሆን ድረስ፣ በህዝቡ አይኖች ፊት ሞገስን ታገኛላችሁ።

፲ ሀ ቅ.መ.መ. ሁለንተና።
፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. ሽማግሌ።
ለ ት.እና ቃ. ፴፯፡፴፪፣ ፶፭፡፴።
ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ስጦታ።
፲፪ ሀ ት.እና ቃ. ፲፣።
፲፬ ሀ ኢ.ያ. ፲፡ ፲፪–፲፬፣
ኢሳ. ፵፱፡ ፷፩፣
ት.እና ቃ. ፶፯፡ ፴፯።
፲፭ ሀ ት.እና ቃ. ፩፡ ፲፫–፲፬።
ለ ት.እና ቃ. ፹፬፡ ፫–፬፣
፹፫፡ ፴፭።
ሐ ት.እና ቃ. ፹፣፹፪፡ ፷፬–፷፮።
ቅ.መ.መ. መስደብ።
፲፮ ሀ ት.እና ቃ. ፹፩፡ ፶፭፣
፹፫፡ ፷፪፣ ፴።
ለ ቅ.መ.መ. መጠበቅ፣ ጠባቂ።
፲፯ ሀ ት.እና ቃ. ፹፣፡ ፴–፣።
፲፱ ሀ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
፳፩ ሀ ት.እና ቃ. ፹፬፡ ፹፫።
ቅ.መ.መ. ኩራት።
፳፭ ሀ ቅ.መ.መ. ሰላም።
፳፮ ሀ ኢዩ. ፪፡ ፲፩።

፳፯ እና አገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግ ማዊ እና የመደብኳቸው ሽማግሌዎቼ የቤቴን ብርታት ለመሰብሰብ ጊዜን እስ ከሚያገኙ ድረስ ᵐበፈርኦን ልብ እንዳደ ረግሁት፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ፣ የህዝቡን ልብ አራራለሁ፣

፳፰ እና ᵐብልህ ሰዎችንም፣ በጃክሰን የግ ዛት ክፍል ውስጥ እና በአካባቢው በሚገ ኙት የግዛት ክፍሎች ውስጥ ᵃሊገዙ የሚች ሉትን መሬቶችን ሁሉ ስለመግዛት የሰጠሁ ትን ትእዛዝ ይፈጸሙ ዘንድ ነው።

፳፱ እነዚህ መሬቶች እንዲገዙ ፍቃዴ ነው፤ እና ከተገዙም በኋላ ቅዱሳኔ በሰ ጠኋቸሁ የቅድስና ᵐህግጋት መሰረት ይወ ስዷቸውም ዘንድ ፍቃዴ ነው።

፴ እና እነዚህ መሬቶች ከተገዙ በኋላ፣ የእስራኤል ᵐሰራዊት በገንዘባቸው የገዙ ትን መሬቶቻቸውን መልሰው በመውሰዳ ቸው፣ እና በእነዚያም የሚገኙትን የጠላቶ ቼን ማማዎች በመጣላቸው፣ እና ጠባቂዎ ቻቸውን በመበተናቸው፣ እና የሚጠሉኝ ጠላቶቼን እስከ ሶስተኛ እና አራተኛ ትው ልዶች ᵃስለተበቀሉልኝ ከበደል ነጻ አደር ጋቸዋለሁ።

፴፩ ነገር ግን በቅድሚያ ሰራዊቴ ታላቅ ይሁን፣ እና እንደጸሀይም የጠራ፣ እንደ ᵐጨረቃ የተዋበ፣ እና ዓርማዎቿ ለሁሉም ህዝብ የሚያስፈራ ይሆንም ዘንድ በፊቴም ᵃይቀደስ፤

፴፪ የዚህ አለም መንግስትም የፅዮን መን ግስት በእርግጥም የአምላካችን እና የእርሱ ክርስቶስ ᵐመንግስት እንደሆነም ለማወቅ ይገደዱ ዘንድ፤ ስለዚህ፣ ለህግጋቷ ᵃተገዥ እንሁን።

፴፫ እውነት እላችኋለሁ፣ በከርትላንድ ምድር ውስጥ ለስሜ እንዲገነባ ባዘዝኩት በቤቴ ውስጥ የቤተክርስቲያኔ ሽማግሌዎች ᵐየመንፈስ ስጦታቸውን ይቀበሉ ዘንድ ፍቃዴ ነው።

፴፬ እና ከቤዛነቷ በኋላ ስለፅዮን እና ᵐስለ ህጓ የሰጠሁት ትእዛዛት ይሟሉ እናም ይፈ ጸሙ።

፴፭ ᵐየጥሪ ቀን ነበር፣ ነገር ግን ለመም ረጫ ቀን ጊዜው መጥቷል፤ እና ᵃብቁ የሆኑ እነርሱ ይመረጡ።

፴፮ እና ᵐየተመረጡትም በመንፈስ ድምፅ ለአገልጋዬ ይገለጣሉ፤ እና እነርሱም ᵃይቀ ደሳሉ፤

፴፯ እና የተቀበሉትን ᵐምክር እስከተ ከተሉ ድረስ፣ ከብዙ ቀናት በኋላ ፅዮንን የሚመለከቱ ነገሮችን ሁሉ ያከናውኑ ዘንድ ሀይል ይኖራቸዋል።

፴፰ ደግሞም እላችኋለሁ፣ ለመቷችሁ ሰዎች ብቻ ሳይሁን ለሁሉም ሰዎች፣ የሰ ላም ሀሳብ አቅርቡ፤

፴፱ እና ᵐየሰላም ᵃአርማ አንሱ፣ እና ለም ድር ዳርቻዎችም ሰላምን አውጁ፤

፴ እና በውስጣችሁ ባለው በመንፈስ ድምፅ መሰረት ለመቷችሁም የሰላም ሀሳብ አቅርቡላቸው፣ እና ᵐሁሉም ነገሮች ለጥ ቅማችሁ አብረው ይሰራሉ።

፴፩ ስለዚህ፣ ታማኝ ሁኑ፤ እነሆ፣ እናም አስተውሉ፣ እስከመጨረሻውም ᵐእኔ ከእ ናንተ ጋር ነኝ። እንዲሁም ይሁን። አሜን።

፳፯ ᵐ ዘፍጥ. ፣ ፡–፣ ። ፳፰ ᵐ ት. እና ቃ. ፡ ። ᵃ ት. እና ቃ. ፣ ፡–፣ ። ፳፱ ᵐ ት. እና ቃ. ፣ ፡ ። ᵃ ቅ.መ.መ. መቀደስ፣ የቅድስና ህግ፣ የትብብር ስርዓት። ፴ ᵐ ት. እና ቃ. ፣ ፡–፣ ፡ ፣ ፡ ፣ ፡ ። ᵃ ት. እና ቃ. ፣ ፡ ። ፴፩ ᵐ መኃ. ፡ ፣ ። ት. እና ቃ. ፡ ፣ ፡ ፣ ፡ ። ᵃ ቅ.መ.መ. ቅድስና።

፴፪ ᵐ ራዕ. ፡ ፣ ፡ ። ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር መንግስት ወይም መንግስተ ሰማያት። ᵃ ቅ.መ.መ. መንግስት። ፴፫ ᵐ ት. እና ቃ. ፣ ፡–፡ ። ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ስጦታ። ፴፬ ᵐ ይህም ት. እና ቃ. ፣ “ህግ” ተብሎ ይታወቃል ማለት ነው። ፴፭ ᵐ ቅ.መ.መ. ጥሪ፣ በእግዚአብሔር መጠራት፣ የተጠራበት። ᵃ ቅ.መ.መ. ብቁ፣ ብቁነት። ፴፮ ᵐ ት. እና ቃ. ፣ ፡ ። ቅ.መ.መ. መምረጥ፣ መረጠ፣ የተመረጠ (ግስ)። ᵃ ቅ.መ.መ. ቅድስና። ፴፯ ᵐ ቅ.መ.መ. ምክር (ስም)። ፴፱ ᵐ ቅ.መ.መ. ሰላም። ᵃ ቅ.መ.መ. ምልክት። ፴ ᵐ ሮሜ ፡ ፣ ፡ ፣ ት. እና ቃ. ፣ ፡ ፣ ፡ ፣ ፡ ። ፴፩ ᵐ ማቴ. ፡ ፣ ፡–፡ ።

ክፍል ፲፤

በህዳር ፳፭፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ ኦሀዮ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ይህ ለኦሊቨር ካውድሪ ታላቅ ወንድም ለሆነው ለዋረን ካውድሪ የተሰጠ ራዕይ ነው።

፩–፫፣ ዋረን ኤ ካውድሪ በሚኖርበት አካባቢ ቀዳሚ መሪ እንዲሆን ተጠርቷል፤ ፬–፭፣ ዳግም ምፅዓት የብርሀን ልጆችን እንደ ሌባ አይደርስባቸውም፤ ፮–፳፣ የቤተክርስቲያኗ ታማኝ አገልጋይነት ታላቅ በረከቶች ይከተሉታል።

፩ አገልጋዬ ዋረን ኤ ካውድሪ [ሀ]በፍሪደም እና በአካባቢዋ ምድር ውስጥ በቤተክርስቲያኔ እንደ ሊቀ ካህናት አመራር እንዲመደብ እና እንዲሾም ፍቃዴ ነው።

፪ ዘለዓለማዊ ወንጌሌንም ይስበክ፣ እና በራሱ ስፍራ ብቻ ሳይሆን፣ በአጠገቡ በሚገኙት የግዛት ክፍሎችም ድምጹን ከፍ ያድርግና ህዝብን ያስጠንቅቅ፤

፫ እና [ሁ]መንግስተ ሰማያትንና ፅድቁንም በትህትና [ለ]በመፈለግ፣ በምሰጠው በዚህ ከፍተኛ እና ቅዱስ ጥሪም ጊዜውን ሁሉ መስዋዕት ያድርግ፣ እና አስፈላጊ ነገሮች ሁሉ ይጨመሩለታል፤ [ሐ]ለሠራተኛ ደመወዙ ይገባዋልና።

፬ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ የጌታ [ሂ]መምጣት [ለ]ቀርቦአል፣ እና [ሐ]ሌባ በሌሊት እንደሚመጣም በአለም ላይ ይደርስል—

፭ ስለዚህ፣ [ሁ]የብርሀን ልጆች ትሆኑ ዘንድም ወገባችሁን አጥብቁ፣ እና ያም ቀን በሌሊት እንደ ሌባ [ለ]አይደርስባችሁም።

፮ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ አገልጋዬ ዋረን ለመንግስቴ በትር ሲሰግድና እራሱን ከተንኮለኞች ሰዎች ሲለይ በሰማይ ደስታ ነበር።

፯ ስለዚህ፣ አገልጋዬ ዋረን የተባረከ ነው፣ ምህረት እሰጠዋለሁና፤ እና ልቡ [ሁ]ግብዝነት ቢኖርበትም፣ በፊቴ ትሁት እስከሆነ ድረስ ከፍ አደርገዋለሁ።

፰ የሚቆምበትም [ሁ]ጸጋ እና ማረጋገጫም እሰጠዋለሁ፤ ታማኝ ምስክርና ለቤተክርስቲያኗም ብርሀን ሆኖ ቢቀጥል በአባቴ [ለ]ቤት አክሊል አዘጋጅቼለታለሁ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፲፯

በሚያዝያ ፲፰፻፴፭ (እ.አ.አ.) አካባቢ፣ በከርትላንድ ኦሀዮ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል ስለክህነት የተሰጠ ራዕይ። ይህ ራዕይ የተመዘገበው በ፲፰፻፴፭ (እ.አ.አ.) ቢሆንም፣ ከቁጥር ፳ እስከ ፴ አብዛኛዎች በህዳር ፲፩፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.) በጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጡ ራዕዮችን የሚያጠቃልሉ ነበሩ። ይህ ክፍል የአስራ ሁለት ቡድንን በየካቲት እና በመጋቢት ፲፰፻፴፭ (እ.አ.አ.) ከተደራጀበት ጋር የተገ

፲፤ ፩ *ሀ* ይህም የሪዶም ከተማ፣ ኒውዮርክ እና አካባቢዋ ማለት ነው።
፫ *ሀ* ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር መንግስት ወይም መንግስተ ሰማያት።
ለ ማቴ. ፮፡ ፴፫።
ሐ ማቴ. ፲፡ ፲፡ ት. እና ቃ. ፴፩፡ ፭።
፬ *ሀ* ያዕ. ፭፡ ፳።
ለ ቅ.መ.መ. የመጨረሻ ቀናት፣ የኋለኛው ቀናት።
ሐ ፩ ተሰ. ፭፡ ፪።
፭ *ሀ* ቅ.መ.መ. ብርሀን፣ የክርስቶስ ብርሀን።
ለ ራዕ. ፲፮፡ ፲፭።
፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. ከንቱ፣ ከንቱነት።
፰ *ሀ* ቅ.መ.መ. ጸጋ።
ለ ዮሐ. ፲፬፡ ፪፣ ኤተር ፲፪፡ ፴፪–፴፬፣ ት. እና ቃ. ፶፬፡ ፪፣ ፷፫፡ ፲፲፭፣ ፹፡ ፭፣ ፹፰፡ ፲፰።

ናኘ ነው። ነቢዩ ምናልባት በቡድናቸው የመጀመሪያዎቹ ሚስዮናውያን በግን ቦት ፲፣ ፲፰፲፱፲፭ (እ.አ.አ.) ለመሄድ በሚዘጋጁበት ጊዜ በነበሩት ፊት ይህን ሳያ ቀርበው አልቀረም።

፩–፯፣ ሁለት ክህነቶች አሉ፡ መልከ ጼዴቅ እና አሮናዊ፤ ፯–፲፪፣ የመልከ ጼዴቅ ክህ ነትን የያዙት በቤተክርስቲያኗ የሀላፊነት ስፍራዎች ሁሉ ለማስተዳደር ሀይል ይኖ ራቸዋል፤ ፲፫–፲፯፣ ኤጲስ ቆጶስ ውጪ ውን ሥርዓት የሚያስተዳድረውን አሮናዊ ክህነትን ያስተዳድራል፤ ፲፰–፳፣ የመልከ ጼዴቅ ክህነት የመንፈሳዊ በረከቶችን ሁሉ ቁልፎች ይሟል፤ የአሮናዊ ክህነት የመ ላዕክትን አገልግሎት ቁልፎችን ይሟል፤ ፳፩–፳፫፣ በአንድነት እና በፅድቅ ውሳ ኔዎቻቸው የሚደረጉባቸው ቀዳሚ አመ ራር፣ አስራ ሁለቱ፣ እና ሰባዎች የአመ ራር ቡድኖችን ይመሰርታሉ፤ ፳፬–፳፱፣ የአባቶች አለቃ ስርዓትም ከአዳም እስከ ኖህ ጀምሮ ተመስርቷል፤ ፳፫–፳፯፣ የጥንት ቅዱሳን በአዳም-ኦንዳይ-አማን ተሰበሰቡ፣ እና ጌታ በእነርሱም ታየ፤ ፳፰–፳፱፣ አስራ ሁለቱ የቤተክርስቲያኗ ሀላፊዎች በስርዓት ያቀናጁ፤ ፳፰–፴፯፣ ኤጲስ ቆጶሳት እንደ እስራኤል ቋሚ ዳኛ ያገለግላሉ፤ ፴፯–፴፱፣ ቀዳሚ አመራርና አስራ ሁለቱ እንደ ቤተ ክርስቲያኗ ከፍተኛ ዳኝነት ስርዓቱን ይመ ሰርታሉ፤ ፴፰–፴፣ የክህነት ፕሬዘደንቶች የየሀላፊነት ቡድኖቻቸውን ያስተዳድራሉ።

፩ በቤተክርስቲያኗ ውስጥ፣ የሌዊ ክህ ነትን ጨምሮ፣ በስም [ሀ]መልከ ጼዴቅና፣ [ለ]አሮናዊ የሚባሉ ሁለት ክህነቶች አሉ።

፪ የመጀመሪያው [ሀ]የመልከ ጼዴቅ ክህ ነት ተብሎ የሚጠራበት ምክንያት መልከ ጼዴቅ ታላቅ ሊቀ ካህን ስለነበር ነው።

፫ ከእርሱ ቀን በፊት እንደ እግዚአብሔር ልጅ [ሀ]ስርዓት ቅዱስ ክህነት ተብሎ የሚ ጠራ ነበር።

፬ ነገር ግን ለኃያል ጌታ ስም ክብር ወይም [ሀ]አምልኮ፣ ስሙን እጅግ በጣም በመደጋ ገም መጠቀምን ለማስወገድ፣ የጥንት ጊዜ ቤተክርስቲያኗ የነበሩት እነርሱ፣ ያን ክህ ነት የመልከ ጼዴቅ ክህነት በማለት ወይም በመልከ ጼዴቅ ስም ጠሩት።

፭ በቤተክርስቲያኗ ውስጥ ያሉ ሌሎቹ ስልጣናት ወይም ሀላፊነቶች ሁሉ ከዚህ ክህነት ጋር [ሀ]የተያያዙ ናቸው።

፮ ነገር ግን ሁለት ክፍሎች ወይም ዋና ክፍሎች አሉ—አንዱ የመልከ ጼዴቅ ክህ ነት ስልጣን፣ እና ሌላው አሮናዊ ወይም [ሀ]ሌዊ ክህነት ነው።

፯ [ሀ]የሽማግሌ ሀላፊነት ከመልከ ጼዴቅ ክህነት በታች የሚሆን ነው።

፰ የመልከ ጼዴቅ ክህነት የፕሬዘደንትነት አመራርን ይይዛል፣ እና በመንፈሳዊ ነገሮች ለማስተዳደር፣ በአለም ዘመኖች ሁሉ በቤ ተክርስቲያኗ ሀላፊነቶች ላይ ሁሉ ሀይል እና [ሀ]ስልጣን አለው።

፱ እንደ መልከ ጼዴቅ ስርዓት ሁሉ፣ የታላቅ ክህነት [ሀ]አመራር በቤተክርስቲያኗ ውስጥ በሚገኙት ሀላፊነቶች ሁሉ የማስተ ዳደር መብት አለው።

፲ [ሀ]ሊቀ ካህናት እንደ መልከ ጼዴቅ ስር ዓት፣ በቀዳሚ አመራር መመሪያ በመንፈ ሳዊ ነገሮች በማስተዳደር ሀላፊነታቸው፣ እና ደግሞም በሽማግሌ አመራር፣ በካህን አመራር (የሌዊው ስርዓት)፣ በመምህር ነት፣ በዲያቆንነት፣ እና በአባል ሀላፊነቶች ለማስተዳደር [ለ]መብት አላቸው።

፲፯ ፩ [ሀ] ቅ.መ.መ. የመልከ ጼዴቅ ክህነት።
[ለ] ቅ.መ.መ. አሮናዊ ክህነት።
፪ [ሀ] ጆ.ስ.ት. ዘፍጥ. ፲፬፡ ፳፫–፴ (ተጨማሪ)፤ ት. እና ቃ. ፹፬፡ ፲፬። ቅ.መ.መ. መልከ ጼዴቅ።
፫ [ሀ] አልማ ፲፫፡ ፫–፲፱፤ ት. እና ቃ. ፳፯፡ ፱፯።
፬ [ሀ] ቅ.መ.መ. ማክበር።
፭ [ሀ] ት. እና ቃ. ፹፬፡ ፳፱፣ ፲፯፡ ፲፱።
፮ [ሀ] ዘዳግ. ፲፡ ፰–፱።
፯ [ሀ] ቅ.መ.መ. ሽማግሌ።
፰ [ሀ] ቅ.መ.መ. ስልጣን።
፱ [ሀ] ት. እና ቃ. ፹፬፡ ፪፣ ፲፯፡ ፳፭፣ ፳፰፣ ፳፭–፳፯፣ ፶፭–፶፯፣ ፶፭–፶፯።
፲ [ሀ] ቅ.መ.መ. ሊቀ ካህን።
[ለ] ት. እና ቃ. ፻፳፭፡ ፴፬–፴፯።

፲፩ ሊቀ ካህን በማይኖርበት ጊዜ ሽማግሌ በእርሱ ምትክ ማስተዳደር ይችላል።

፲፪ ሊቀ ካህን እና ሽማግሌ፣ ከቤተክርስቲያኗ ቃል ኪዳናት እና ትእዛዛት በመስማማት፣ በመንፈሳዊ ነገሮች ያስተዳድሩ፤ እና ከፍተኛ ባለስልጣናት በማይኖሩበት ጊዜ፣ በእነዚህ የቤተክርስቲያኗ ሀላፊነቶች ሁሉ የማስተዳደር ሀላፊነት አላቸው።

፲፫ ሁለተኛው ክህነት ᵇአሮናዊ ክህነት ተብሎ ይጠራል፣ ምክንያቱም ᵃበአሮን እና በዘሩ፣ በትውልዶቻቸው ሁሉ፣ የተሰጣቸው ነበርና።

፲፬ አነስተኛው ክህነት ተብሎ የሚጠራበት ምክንያትም ከታላቁ፣ ወይም ከመልከ ጼዴቅ ክህነት፣ ጋር ᵇየተያያዘ ስለሆነ እና ለውጪአዊ ስርዓቶችን ለማስተዳደር ሀይል ስላለው ነው።

፲፭ ᵇየኤጲስ ቆጶስ አመራርም የዚህ ክህነት ስልጣን አመራር ነው፣ እና የዚህንም ቁልፎች ወይም ስልጣን ይዟል።

፲፮ የአሮን ᵇእውነተኛ ተወላጅ ካልሆነ በስተቀር፣ ማንም ሰው ለዚህ ሀላፊነት፣ ወይም የዚህን ክህነት ቁልፎች ለመያዝ፣ ህጋዊ መብት የለውም

፲፯ ነገር ግን እንደ የመልከ ጼዴቅ ክህነት ሊቀ ካህን በአነስተኛ ሀላፊነቶች ሁሉ ለማስተዳደር ስልጣን ስላለው፣ የአሮን እውነተኛ ተወላጅ በማይገኝበት ጊዜ፣ በመልከ ጼዴቅ ክህነት ᵇአመራር በኩል ለዚህ ሀይል ከተጠራና ከተለየ እና ᵃከተሾመ በኋላ በኤጲስ ቆጶስ ሀለፊነት ለማስተዳደር ይችላል።

፲፰ የከፍተኛው፣ ወይም የመልከ ጼዴቅ ክህነት፣ ሀይል እና ስልጣን በቤተክርስቲያኗ መንፈሳዊ በረከቶች ላይ ሁሉ ᵇቁልፎችን መያዝ ነው።

፲፱ በተጨማሪም፣ የመንግስተ ሰማያትን ᵇሚስጥራት ለመቀበል ልዩ መብት እንዲኖረው፣ ሰማያት ለእነርሱ እንዲከፈቱላቸው፣ ከበኩሩ ቤተክርስቲያንና ᵃከአጠቃላይ ተሰብሳቢዎች ጋር እንዲገናኝ፣ እና ከእግዚአብሔር አብ እና ከአዲስ ኪዳን ᶜአማላጅ ከሆነው ከኢየሱስ ጋር መገናኘትን እና በእነርሱም መገኘት ለመደሰት ነው።

፳ የአነስተኛው ክህነት፣ ወይም የአሮናዊ ክህነት፣ ሀይል እና ስልጣን፣ ከቃል ኪዳናት እና ትእዛዛት ጋር በመስማማት፣ የመላእክትን አገልግሎት ᵇቁልፎች ለመያዝ እና የውጪአዊ ᵃስርዓቶች የሆኑትን የወንጌሉን ፊደል እና ለኃጢአት ᶜስርየት የንስሐ ᵐጥምቀትን ለማስተዳደር ነው።

፳፩ ስለአስፈላጊነታቸውም ፕሬዘደንቶች፣ ወይም ከተለያዩ ከእነዚህ ሁለት ክህነቶች ውስጥ በተላያዩ ሀላፊነቶች ከተሾሙት መካከል የሚመጡ ወይም የሚሾሙ መሪዎች አሉ።

፳፪ ᵇከመልከ ጼዴቅ ክህነትም፣ ሶስቱ ሊቀ ካህን ᵃመሪዎች በቡድኑ ተመርጠው፣ ለሀለፊነቱ ተመድበውና ተሹመው፣ እና በቤተክርስቲያኗ እምነት፣ ታማኝነት፣ እና ጸሎት ᶜተደግፈው የቤተክርስቲያኗን አመራር ቡድን ይመሰርታሉ።

፳፫ ተጓዥ ᵇአስራ ሁለቱ አማካሪዎች አስራ ሁለቱ ᵃሐዋርያት፣ ወይም ለአለም ሁሉ የክርስቶስ ስም ልዩ ምስክሮች፣ ተብለው ተጠርተዋል—በዚህም በጥሪአቸው

፲፫ ᵇ ቅ.መ.መ. አሮናዊ ክህነት።
ᵃ ቅ.መ.መ. አሮን፣ የሙሴ ወንድም።
፲፬ ᵇ ት. እና ቃ. ፳፡ ፶፪፣ ፸፯፡ ፭።
፲፭ ᵇ ቅ.መ.መ. ኤጲስ ቆጶስ።
፲፮ ᵇ ት. እና ቃ. ፳፳፡ ፲፡–፳፩፣ ፸፯፡ ፳፳–፳፭።
፲፯ ᵇ ት. እና ቃ. ፳፳፡ ፲፭።
ᵃ ቅ.መ.መ. መሾም፣ ሹመት።
፲፰ ᵇ ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
፲፱ ᵇ አልማ ፲፪፡ ፱–፲፭፣ ት. እና ቃ. ፳፫፡ ፳፫፣ ፹፬፡ ፲፱–፳፪።
ᵃ ቅ.መ.መ. ስነስርዓቶች።
ᵇ ቅ.መ.መ. ሚስጥሮች።
ᵃ ዕብ. ፲፪፡ ፳፪–፳፬።
ᶜ ቅ.መ.መ. አማላጅ።
፳ ᵇ ት. እና ቃ. ፲፫፣ ፹፬፡ ፳፪–፳፯።
ᵃ ቅ.መ.መ. ስነስርዓቶች።
ᶜ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ስርየት።
ᵐ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣ መጥመቅ።
፳፪ ᵇ ቅ.መ.መ. የመልከ ጼዴቅ ክህነት።
ᵃ ት. እና ቃ. ፮፡ ፫፣ ፮፣ ፲፯፡ ፱፣ ፳፫–፳፮፣ ፫፫፡ ፹፬፡ ፲፪–፲፪።
ᶜ ቅ.መ.መ. የቤተክርስቲያን መሪዎችን መደገፍ።
፳፫ ᵇ ት. እና ቃ. ፲፯፡ ፴፫–፴፭።
ᵃ ቅ.መ.መ. ሐዋሪያ።

ሀላፊነታቸው ከቤተክርስቲያኗ ሌሎች ሀላፊዎች ጋር ይለያያሉ።

፳፬ እና ከዚህ በፊት ከተጠቀሱት ሶስት ፕሬዘደንቶች ጋረ እኩል ስልጣን እና ሀይል ያለው ቡድንም ይሰራሉ።

፳፭ ᵐሰባዎቹ ወንጌልን እንዲሰብኩ፣ እና ለአህዛብና በአለም ሁሉ ልዩ ምስክሮች እንዲሆኑ ተጠርተዋል—በዚህም በጥሪአቸው ሀላፊነታቸው ከቤተክርስቲያኗ ሌሎች ሀላፊዎች ጋር ይለያያሉ።

፳፮ እና ከተጠቀሱት አስራ ሁለቱ ልዩ ምስክሮች ወይም ሐዋርያት ጋር እኩል ስልጣን እና ሀይል ያለው ቡድንም ይሰራሉ።

፳፯ በማንኛቸውም በእነዚህ ቡድኖች የሚያደርጉ እያንዳንዱ ውሳኔዎች በአንድ ድምፅ መሆን አለባቸው፤ ይህም ማለት፣ እርስ በራስ ውሳኔዎቻቸው አንድ ሀይል ወይም ተቀባይነት እንዲኖራቸው ለማድረግ፣ የእያንዳንዱ ቡድን እያንዳንዱ አባል በውሳኔው መስማማት አለባቸው—

፳፰ ሁኔታዎች በተቃራኒ እንዲሆን በማያስችሉበት ጊዜም አብላጫዎቹ ቡድንን መስራት ይችላሉ—

፳፱ ጉዳዩ ይህ ካልሆነ በስተቀር፣ ውሳኔዎቻቸው በመልከ ጼዴቅ ስርዓት ተሹመው የነበር እና ጻድቅና ቅዱስ ሰዎች እንደነበሩት የጥንት ሶስት ፕሬዘደንቶች ውሳኔዎች እንደነበራቸው አንድ አይነት በረከቶች መብት አይኖራቸውም።

፴ የእነዚህ ቡድኖች፣ ወይም የማንኛቸውም፣ ውሳኔዎችም ሁሉ ᵐፅድቅ፣ በቅድስና፣ እና ልብን በማዋረድ፣ በየዋህነትና በትዕግስት፣ እና በእምነት፣ እና ᵃበበጎነት፣ እና በእውቀት፣ ራስን በመግዛት፣ በመፅናት፣ እግዚአብሔርን በመምሰል፣ በወንድማማች መዋደድ እና በፍቅር ይድረሱ፤

፴፩ ምክንያቱም የተሰሩ ቃሉ እነዚህ ነገሮች በእነርሱ አብዝተው የሚገኙ ቢሆን በጌታ እውቀት ᵐፍሬ የሌላቸው አይሆኑም የሚል ነውና።

፴፪ እና እነዚህ ቡድኖች ማንኛውንም ውሳኔ ያለፅድቅ ባለመሆን የሰሩበት ጉዳይ ካለ፣ ይህም የቤተክርስቲያኗ መንፈሳዊ ባለስልጣናት በሆኑት በተለያዩ ቡድኖች አጠቃላይ ተሰብሳቢዎች ፊት ይቅረብ፤ አለበለዚያ ለውሳኔአቸው ምንም ይግባኝ አይኖርም።

፴፫ አስራ ሁለቱ፣ በሰማይ ከተመሰረተው ጋር በመስማማት፣ መጀመሪያ ወደ ᵐአህዛብ እና ሁለተኛም የአይሁዶች ቤተክርስቲያኗን ለመገንባት እና የእርሷን ጉዳዮች በሀገሮች ውስጥ ሁሉ ለመቆጣጠር፣ በቤተክርስቲያኗ አመራር መሪነት በጌታ ስም በማስተዳደር የሚጓዙ ከፍተኛ ሽንጎዎች ናቸው።

፴፬ ሰባዎች፣ ᵐበአስራ ሁለቱ ወይም በሚጓዙት ከፍተኛ ሽንጎ አመራር በኩል፣ መጀመሪያ ወደ አህዛብ እና ሁለተኛም ወደ አይሁዶች፣ ቤተክርስቲያኗን በመገንባት እና የእርሷን ጉዳዮች በሀገሮች ውስጥ ሁሉ በመቆጣጠር በጌታ ስም ይሰሩ—

፴፭ አስራ ሁለቱ፣ መጀመሪያ ወደ አህዛብ እና ሁለተኛም ወደ አይሁዶች፣ በመላክ፣ ቁልፎችን በመያዝ፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል በማወጅ በሮችን ለመክፈት ተልከዋል።

፴፮ በፅዮን ካስማዎች የአካባቢው ᵐከፍተኛ ሽንጎዎች በቤተክርስቲያኗ ጉዳይ ላይ፣ በውሳኔዎቻቸው ሁሉ ከአመራር ቡድን ወይም ከተጓዥ ከፍተኛ ሽንጎ ጋር እኩል ስልጣን ያላቸው ቡድኖች ያቋቁሙ።

፴፯ በፅዮን ውስጥ ያሉት ከፍተኛ ሽንጎ በፅዮን ካስማ ውስጥ ካሉት የአስራ ሁለቱ ቡድኖች ጋር በውሳኔዎቻቸው ሁሉ፣ በቤ

፳፭ *ሀ* ቅ.መ.መ. ሰባ።
፴ *ሀ* ት. እና ቃ. ፲፳፭፡ ፴፯።
ቅ.መ.መ. ጻድቅ፡ ጽድቅ።
ለ ት. እና ቃ. ፲፳፭፡ ፴፩።

ቅ.መ.መ. በጎነት።
፴፩ *ሀ* ፪ ጴጥ. ፩፡ ፭–፰።
፴፫ *ሀ* ፩ ኔፊ ፲፫፡ ፴፪፤
፲ ኔፊ ፲፯፡ ፴–፲፫፤
ት. እና ቃ. ፯፡ ፰–፱።
፴፬ *ሀ* ት. እና ቃ. ፲፲፪፡ ፳፩።
፴፮ *ሀ* ቅ.መ.መ. ከፍተኛ ሽንጎ።

ተክርስቲያኗ ጉዳዮች እኩል ስልጣን ያለው ቡድን ያቋቁማሉ።

፴፫ ለመስበክ እና ወንጌሉን ለማስተዳደር እርዳታ ሲያስፈልጋቸው፣ በማንም ሌሎች ምትክ፣ ᵐሰባዎችን መጥራት የሚጓዙት ከፍተኛ ሽንጎ ሀላፊነት ነው።

፴፬ በትልቁ የቤተክርስቲያኗ ቅርንጫፎች ውስጥ ሁሉ፣ በራዕይ እንደሚመደቡላቸው፣ ᵐወንጌል ሰባኪዎችን መሾም የአስራ ሁለቱ ሀላፊነት ነው—

እበሉ መካከል ይሄድ ዘንድ በጣም ጥቂት በሆነ የመርከብ መሪ ᵐጥቅም እንደሚያገኝ ታውቃላችሁ።

፲፯ ስለዚህ፣ ውድ ወንድሞች፣ በሀይላችን ያሉትን ነገሮች ሁሉ ᵐበደስታ እናድርግ፤ ከዚያም በእርግጠኝነት የእግዚአብሔር የሚያደርገውን ᵃማዳን ለማየት እንቁም እና የክንዱንም መገለጥ እንጠባበቅ።

ክፍል ፪ ፳፭

በጥር ፲፱፣ ፲፰፻፵፭ (እ.አ.አ.) በናቩ ኢለኖይ ውስጥ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተሰጠ ራዕይ። በእነርሱ ላይ በመንግስት ባለስልጣናት በተደረጉባቸው ተጨማሪ ስደቶችና ህገ ወጥ ስራዎች ምክንያት፣ ቅዱሳን ሚዙሪን ለቅቀው ለመውጣት ተገድደው ነበር። በጥቅምት ፳፯፣ ፲፰፻፵፭ (እ.አ.አ.) በሚዙሪ አስተዳዳሪ ሊበርን ደብሊው ጋግስ በተሰጠው ዘር የማጥፋት ትእዛዝ ምንም ሌላ ምርጫ አልሰጣቸውም። በ፲፰፻፵፮ (እ.አ.አ.)፣ ይህ ራዕይ ሲሰጥ፣ በቀድሞ ኮመርስ መንደር፣ ኢለኖይ ስፍራ ላይ የተመሰረተው የናቩ ከተማ በቅዱሳኑ ተገንብቶ ነበር፣ እና በዚህም የቤተክርስቲያኗ ጠቅላይ መምሪያ ተመስርቶ ነበር።

፩–፲፬፣ ጆሴፍ ስሚዝ ለዩናይትድ ስቴትስ ፕሬዘደንት፣ ለአስተዳዳሪዎች፣ እና ለሁሉም ሀገሮች መሪዎች ወንጌልን እንዲያውጅ ታዘዘ፤ ፲፭–፳፩፣ በህይወት ከሚኖሩትና ከሞቱት መካከል ሀይረም ስሚዝ፣ ዴቪድ ደብሊው ፓትተን፣ ጆሴፍ ስሚዝ ቀዳማዊ፣ እና ሌሎች ለቅንነታቸው እና ለምግባር መልካምነታቸው ተባርከዋል፤ ፳፪–፳፰፣ ቅዱሳን እንግዳዎችን የሚቀበሉበትን ቤት እና ቤተመቅደስን እንዲገነቡ ታዝዘዋል፣ ፳፱–፴፯፣ የሙታን ጥምቀት በቤተመቅደስ ውስጥ ይፈጸም፤ ፴፰–፴፡ የጌታ ህዝብ ለቅዱስ ስርዓቶች ማከናወኛ ዘወትር ቤተመቅደስን ይገነባሉ፤ ፴፩–፴፭፣ ቅዱሳን በጠላቶቻቸው ክፋት ምክንያት በጃክሰን የግዛት ክፍል ቤተመቅደስን ባለመገንባታቸው ይሁንታን አግኝተዋል፤ ፴፮–፴፱፣ ለናቩ ቤት መገንቢያ መመሪያዎች ተሰጥተዋል፤ ፴፡–፴፯፣ ሀይረም ስሚዝ ፕትሪያርክ እንዲሆን፣ ቁልፎችን እንዲቀበል፣ እና በአሊቨር ካውድሪ ስፍራ እንዲቆም ተጠርቷል፤ ፴፯–፳፰፣ ውልያም ሷው እና ሌሎች በአገልግሎታቸው ተመክረዋል፤ ፳፰፣–፳፱፣ አጠቃላይ እና የአካባቢ ባለስልጣናት ከሀላፊነታቸው እና ተባባሪ ግንኙነት ካላቸው ቡድኖች ጋር ተጠርተዋል።

፩ በእውነት፣ ጌታ ለአንተ፣ አገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ፣ እንዲህ ይላል፣ አንተ ባደረካቸው መስዋዕት እና እውቅናዎች በተቀበልክባቸው ተደስቼአለሁ፤ በምድር ᵐደካማ ነገሮች ጥበቤን አሳይ ዘንድ፣ ለዚህም ምክንያት ነው ያስነሳሁህ።

፪ ጸሎቶችህ በፊቴ ተቀብዬአቸዋለሁ፤ እና ለእነዚህም መልስ በመስጠት እንዲህ እልሀለሁ፣ አሁንም ወዲያው ወንጌሌን፣ እና በቤተመንግስት ምሳሌነት በመንጠር የምትብረቀረቀው የፅዮን የማዕዘን ራስ ድንጋይ እንድትሆን ስለተከልኳት ᵐካስማ በቅድስና እንድታውጅ ተጠርተሀል።

፫ ይህም እወጃ ለአለም ᵐነገስታት ሁሉ፣

፲፯ ᵐ ያዕ. ፫፡፩፤ አልማ ፴፯፡፯–፯፣ ት. እና ቃ. ፳፩፡ ፴፫፡ ፲፯ ᵐ ት. እና ቃ. ፶፱፡ ፲፭።

ᵃ ዘፀአ. ፲፭፡ ፲፫። ፪ ᵐ ፩ ቆሮ. ፩፡ ፳፯–፳፰፤ ት. እና ቃ. ፩፡ ፲፱፤ ፴፭፡ ፲፫።

፪ ᵐ ቅ.መ.መ. ካስማ። ፫ ᵐ መዝ. ፻፲፱፡ ፵፯፣ ማቴ. ፲፡ ፲፰፤ ት. እና ቃ. ፩፡ ፳፫።

በዚህም አራት ማዕዘናት፣ ለተከበረው እንደ ፕሬዘደንት ለተመረጠው፣ እና ለተከበሩት ለምትኖርበት አገር እና በውጪ ለተበተኑት የምድር አገሮች አስተዳዳሪዎች ሁሉ ይደረግ።

፱ ይህንም ᵐበትህትና መንፈስ እና፣ ይህን በምትፅፍበት ጊዜ በውስጥህ በሚገኘው በመንፈስ ቅዱስ ሀይል ይጻፍ፤

፲ ስለእነዚያ ነገስታት እና ባለስልጣናት፣ እንዲሁም ወደፊት በሚመጣው ጊዜ ስለሚ ደርስባቸው፣ ያለኝን ፈቃድ በመንፈስ ቅዱስም አማካይነት ታውቅ ዘንድ ይሰጥሀል።

፲፩ እነሆ፣ የፅዮንን ብርሀን እና ክብር እንዲመለከቱ ልጠራቸው ነውና፣ የመሞገሷ ዘመንም ቀርቧልና።

፲፪ ስለዚህ በጎላ ድምፅ እወጃ፣ እና በምስክርህ ጥራቸው፣ እና አትፍራቸው፣ ደግሞም ያለምክንያት ይተዉ ዘንድ፣ እነርሱ እንደ ᵐሣር ናቸው እና ክብራቸውም ሁሉ እንደ ሣር አበባ ይረግፋልና—

፲፫ እና አገልጋዮቼን እና የገለጥኩላቸውን ምስክሬን ቢቃወሙ፣ ጥርስ ᵐማፋጨት በሚኖርበት የክፉዎችንም እድል ፈንታ ከግብዞች ጋር በማደርግበት ጊዜ፣ የፊቴንም መጋረጃ ሳወልቅ፣ በጉብኝት ቀን ይጎበኛሉ።

፲፬ ደግሞም፣ ብዙዎቹንም ለእናንተ ጥቅም፣ ወደ እውነትም ᵐብርሀን እና አህዛብም ወደ ዘለአለማዊነት ወይም ወደ ፅዮን ወደ ዘለአለማዊ ክብር ይመጡ ዘንድ በአይኖቻቸውም ፊት ጸጋን ታገኙ ዘንድ፣ እጎበኛቸዋለሁ እናም ልቦቻቸውንም አለሰልሳለሁ።

፲ በማታስቡበት ᵐሰዓት፣ የጉብኝቴ ቀን ፈጥኖ ይመጣል፤ እና የህዝቤ ደህንነት እና ከእነርሱም የሚቀሩት መሸሸጊያቸው የት ይሆናል?

፲፩ ተነሱ፣ የምድር ነገስታት ሆይ! ከወርቃችሁና ከብራችሁ ጋር ህዝቤን ወደ መርዳት፣ ወደፅዮን ሴት ልጆች ቤት ኑ።

፲፪ ደግሞም፣ እውነት እልሀለሁ፣ አገልጋዬ ሮበርት ቢ. ቶምሰን ይህን እወጃ ለመጻፍ ይርዳህ፣ እና ከአንተ ጋር ይሁን፣ በእርሱ ተደስቻለሁና፤

፲፫ ስለዚህ፣ ምክርህን ያድምጥ፣ እና በሚበዙ በረከቶች እባርከዋለሁ፤ ከዚህ ጀምሮ በሁሉም ነገሮች ታማኝ እና እውነተኛ ይሁን፣ እና በአይኖቼም ታላቅ ይሆናል።

፲፬ ነገር ግን በእጆቼ ስለምጠብቅበት ᵐመጋቢነትም ያስታውስ።

፲፭ ደግሞም፣ እውነት እልሀለሁ፣ አገልጋዬ ᵐሀይረም ስሚዝ የተባረከ ነው፤ እኔ ጌታ በልቡ ᵃቅንነት፣ እና በፊቴ ትክክል የሆነውን ስለሚወድ እወደዋለሁና፣ ይላል ጌታ።

፲፮ እንደገናም፣ አገልጋዬ ጆን ሲ. በነት፣ ቃሌን ለነገስታት እና ለምድር ህዝቦች በመላክ ስራህ ይርዳህ፤ እንዲሁም ከአንተ ከአገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝም ጋር በስቃይህ ሰአት ከጎንህ ይቁም እና ᵐምክርንም የሚቀበል ቢሆን ዋጋው አይወድቅም።

፲፯ እና ፍቅሩም ታላቅ ይሆናልና፣ ይህንም ቢያደርግ የእኔ ይሆናልና፣ ይላል ጌታ። ቢቀጥልም የምቀበለውን፣ የሰራውን ስራ ተመልክቻለሁ፣ እና በበረከቶችን እና ታላቅን የክብር አክሊል እጭንለታለሁ።

፲፰ ደግሞም፣ አገልጋዬ ላይመን ዋይት በፅዮን በትሁትነት መንፈስ፣ በአለም ፊት እየመሰከረልኝ በመስበክ እንዲቀጥል ፍቃዴ እንደሆነ ይህን እልሀለሁ፤ እና ᵐበንስርም ክንፍ ላይ እንደሚሆንም እሸከመዋለሁ፤ እና ግርማ እና ክብርንም ለእራሱ እና ለስሜ ያገኛል።

፩ ᵐ ቅ.መ.መ. ገር፣ ገርነት።
፲ ᵐ መዝ. ፲፫፡ ፲፩–፲፮፤ ኢሳ. ፵፡ ፮–፰፤ ፩ ጴጥ. ፩፡ ፳፬–፳፭።
፰ ᵐ ማቴ. ፰፡ ፲፪፤ አልማ ፵፡ ፲፫፤ ት. እና ቃ. ፲፭፡ ፣፲፩፤ ፲፲፪፡ ፳፩።
፱ ᵐ ኢሳ. ፰፡ ፩–፱። ቅ.መ.መ. ብርሀን፣ የክርስቶስ ብርሀን።
፲ ᵐ ማቴ. ፳፬፡ ፴፬፤ ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፡ ፴፰።
፲፩ ᵐ ቅ.መ.መ. መጋቢ፣ መጋቢነት።
፲፭ ᵐ ቅ.መ.መ. ስሚዝ፣ ሀይረም። ᵃ ቅ.መ.መ. ቅንነት።
፲፮ ᵐ ቅ.መ.መ. ምክር (ስም)።
፲፰ ᵐ ዘፀአ. ፲፱፡ ፩፤ ኢሳ. ፵፡ ፴፩።

፲፱ ስራውንም ሲጨርስ፣ በዚህ ጊዜ ከእኔ ጋር እንዳለው እንደ አገልጋዬ ᵐዴቪድ ፓትተን እና ደግሞም እንደ አገልጋዬ ᵃኤድዋርድ ፓርትሪጅ፣ እና ደግሞም፣ እርሱም የእኔ ነውና፣ በአብርሐም ᵇጋር ቀኝ እንደተቀመጠው፣ የተባረከው እና በቅድስና ያረጀው አገልጋዬ ᶜጆሴፍ ስሚዝ፣ ቀዳማዊ ወደ እኔም ዘንድ እቀበለዋለሁ።

፳ ደግሞም፣ እውነት እልሀለሁ፣ አገልጋዬ ጆርጅ ሚለር ᵃአታላይ አይደለም፤ በልቡ ቅንነትም ሊታመን ይቻላል፤ እና ለእኔ፣ ለጌታ፣ ለምስክሬ ባለው ፍቅር ምክንያትም እወደዋለሁ።

፳፩ ስለዚህ እልሀለሁ፣ እንደ አገልጋዬ ኤድዋርድ ፓርትሪጅ፣ የቤቴን ቅድስና ይቀበል ዘንድ፣ በድሀ ህዝቤ ራዕይ ላይ በረከቶችን ይሰጥ ዘንድ ᵃየኤጲስ ቆጶስ አመራር ሀላፊነትንም በራሱ ላይ አትምለታ ለሁ፣ ይላል ጌታ። አገልጋዬ ጆርጅን ማንም ሰው አይጥላው፣ እኔን ያከብረኛልና።

፳፪ አገልጋዬ ጆርጅ፣ እና አገልጋዬ ላይ መን፣ እና አገልጋዬ ጆን ስናይደር፣ እና ሌሎችም አገልጋዬ ጆሴፍ እንደሚያሳያቸው አይነት፣ ደግሞም ለእነርሱ በሚያሳያቸው ስፍራ ለስሜ ᵃቤት ይገንቡ።

፳፫ እና ይህም ለማረፊያ ቤት፣ እንግዶች ከሩቅ ስፍራ መጥተው የሚያርፉበት ይሁን፤ ስለዚህ የደከመው ᵃተጓዥ የጌታን ቃል፣ እና ለፅዮን የመደብኩትን ᵇየማዕዘን ራስ ድንጋይ ሲያሰላስል ጤና እና ደህንነትን ያገኝ ዘንድ መልካም፣ ለተቀባይነትም ያለው ብቁ ቤት ይሁን።

፳፬ ይህ ቤት በስሜ ቢገነባ እና የተመደበበት አስተዳዳሪ ምንም የሚያረክሰውን ነገር እንዲገባበት እስካልፈቀደ ድረስ የጤና መኖሪያ ይሆናል። ቅዱስ ይሆናል፣ አለዚያ ጌታ አምላካችሁ አይኖርበትም።

፳፭ ደግሞም፣ እውነት እልሀለሁ፣ ቅዱሳኔ ከእሩቅ ስፍራዎች ይምጡ።

፳፮ እና ፈጣን መልእክተኞች ላኩ፣ አዎን፣ ምርጥ መልእክተኞችንም፣ እና እንዲህም በሏቸው፥ ከሁሉም ወርቆቻችሁ እና ከብሮቻችሁ፣ እና ከውድ ድንጋዮቻችሁ፣ እና ከሁሉም ጥንታዊ ንብረታችሁ ጋር ኑ፤ እና እውቀት ካላቸውም ከጥንቶቹ ጋር የሚመጡትም ይምጡ፣ እና የባርሰነቱን ዛፍ፣ እና የጥዱን ዛፍ፣ እና የአስታውን ዛፍ ከምድር ውድ ዛፎች ሁሉ ጋር አምጡ፤

፳፯ እና ከብረት፣ ከመዳብ፣ እና ከነሀስ፣ እና ከዚንክ፣ እና ከምድር ውድ ነገሮች ሁሉ ጋር፤ እና ከሁሉም በላይ ልዑል ᵐእንዲኖርበት፣ በስሜም ᵃቤት ስሩ።

፳፰ ከእናንተ የጠፋውን ወይም የወሰደውን፣ እንዲሁም የክህነት ሙላትን፣ ᵐደግሞ የሚመልስበት እና የሚመጣበት በምድር ላይ ምንም ስፍራ የለምና።

፳፱ እነርሱ፣ ቅዱሳኔ፣ ለሙታን ᵐይጠመቁ ዘንድ፣ በምድርም ላይ ᵃየማጥመቂያ ገንዳ የለምና—

፴ ይህ ስነ ስርዓት በቤቴ ውስጥ ተገቢ ነውና፣ እና ቤት ለእኔ ለመገንባት በማትችሉበት በድህነታችሁ ቀናቶች በስተቀር፣ እኔ ልቀበልበት አልችልም።

፴፩ ነገር ግን ቅዱሳኔ ሁሉ በስሜ ᵐቤት እንድትገነቡ አዛችኋለሁ፤ እና ለእኔ ቤት የምትገነቡበት ብቁ ጊዜም እሰጣችኋለሁ፤ እና በዚህም ጊዜ ጥምቀቶቻችሁ በእኔ ተቀባይ ይሆናሉ።

፲፱ ᵐ ት. እና ቃ. ፻፳፬፡ ፻፴።
ቅ.መ.መ. ፓተን፣ ዴቪድ ደብሊው።
ᵃ ቅ.መ.መ. ፓርትሪጅ፣ ኤድዋርድ።
ᵃᵃ ት. እና ቃ. ፻፴፯፡ ፻፴–፴፩።
ᵐ ቅ.መ.መ. ስሚዝ፣ ጆሴፍ ቀዳማዊ።
፳ ᵐ ቅ.መ.መ. ተንኮል።
፳፩ ᵐ ት. እና ቃ. ፻፲፩፡ ፱።
ᵃ ቅ.መ.መ. ኤጲስ ቆጶስ።
፳፪ ᵐ ት. እና ቃ. ፻፳፬፡ ፻፲–፲፩።
፳፫ ᵐ ዘዳግ. ፴፩፡ ፲፪፣ ማቴ. ፳፭፡ ፴፭፣ ፴፷።
ᵃ ት. እና ቃ. ፻፳፬፡ ፪።
፳፭ ᵐ ዘፀአ. ፳፭፡ ፳፣ ት. እና ቃ. ፻፲፯፡ ፲፭–፲፯።
ᵃ ት. እና ቃ. ፻፱፡ ፭።
ᵃᵃ ቅ.መ.መ. ቤተመቅደስ፣ የጌታ ቤት።
፳፮ ᵐ ቅ.መ.መ. የወንጌል ዳግም መመለስ።
፳፱ ᵐ ፩ ቆሮ. ፲፭፡ ፳፱፣ ት. እና ቃ. ፻፳፯፡ ፯፣ ፻፴፯፡ ፴፣ ᵐᵐ ቅ.መ.መ. ለሙታን ደህንነት፣ ጥምቀት፣ መጥመቅ—ለሙታን መጠመቅ።
ᵃ ት. እና ቃ. ፻፳፯፡ ፲፣ ᵐ
፴፩ ᵐ ት. እና ቃ. ፻፲፯፡ ፲።

፴፪ ነገር ግን፣ እነሆ፣ ከዚህ ምደባ በኋላ ለሙታን የምታደርጉት ጥምቀት በእኔ ዘንድ ተቀባይነት የለውም፤ እና እነዚህንም ነገሮች በተመደበላቸው ጊዜ መጨረሻ ላይ ባታደጉት ከሙታኖቻችሁ ጋር እንደ ቤተ ክርስቲያን ትወገዳላችሁ፣ ይላል ጌታ አም ላካችሁ።

፴፫ እውነት እላችኋለሁ፣ ለሙታን የጥ ምቀት ስርዓት የሚገባበት፣ እና አለም ከመ መስረቷ በፊት ጀምሮ ለዚህም አላማ የዋ ለውን ቤቴን ለመገንባት ብቁ ጊዜ ካገኛ ችሁ በኋላ፣ ለሙታኖቻችሁ የምትጠመ ቁት በእኔ ዘንድ ተቀባይነትን አያገኝም።

፴፬ ክብር እና ግርማ ትቀበሉ ዘንድ፣ ለቅ ዱስ ክህነት ስልጣን [ሀ]ቁልፎች የሚሾሙት በዚህም ውስጥ ነውና።

፴፭ ከዚህ ጊዜም በኋላ፣ በመካከላችሁ በየአካማቢው የተበተኑት የሙታን ጥም ቀቶቻችሁ በእኔ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው አይደሉም፣ ይላል ጌታ።

፴፮ በፅዮን እና ካስማዎቹ፣ እና በኢየሩሳ ሌም፣ [ሁ]ለመሸሸጊያነት በመደብኳቸው በእ ነዚያ ስፍራዎች ውስጥም ለሙታኖቻችሁ ጥምቀት ስፍራ እንዲሆኑ ተመድበዋል።

፴፯ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ በስሜ በተሰራው ቤት ውስጥ ካልፈጸማ ችሁት በስተቀር፣ [ሂ]መታጠባችሁንስ ለእኔ ዘንድ እንዴት ተቀባይነት ይሆራቸዋል?

፴፰ በዱር ተሸክመው ይወስዱት ዘንድ ነው ሙሴን [ሃ]ታቦት እንዲሰራ ያዘዝኩት፣ እና ከአለም ፍጥረት በፊት ተደብቀው የነበ ሩት ስርዓቶችን ይገልጥም ዘንድ ነው በቃል ኪዳን ምድርም [ሄ]ቤት እንዲሰራ ያዘዝኩት።

፴፱ ስለዚህ፣ እውነት እላችኋለሁ፣ [ሁ]መቀ ባታችሁ፣ እና መታጠባችሁ፣ እና ለሙ ታን [ሀ]መጠመቃችሁ፣ እና [ሁ]የክብር ስብሰ ባዎቻችሁ፣ እና ለሌዊ ልጆች [ሂ]መስዋዕት እና ንግግርን በምትቀበሉበት [ሃ]ቅዱስ ስፍ ራዎቻችሁ ውስጥ ለሚኖራችሁ የእግዚአ ብሔር ቃላት መታሰቢያ፣ እና ለደንቦቻ ችሁ እና ለፍርዶቻችሁ፣ ለራዕያት መጀ መሪያ እና ለፅዮን መመስረት፣ እና ለእር ሷም ማዘጋጃ ቤት ግርማ፣ ክብር፣ እና መን ፈሳዊ ስጦታ፣ ለቅዱስ ስሜ ህዝቤ ሁልጊዜ እንዲገነቡ በሚታዘዙበት በቅዱስ ቤቴ ስነ ስርዓት የተሾሙ ናቸው።

፴ እና እውነት እላችኋለሁ፣ ስነ ስርዓቶ ቼን ለህዝቤ በዚህ ውስጥ እገልጥ ዘንድ፣ ይህም ቤት በስሜ ይሰራ፤

፴፩ ከአለም መመስረት በፊት [ሀ]ተሰው ረው የነበሩትን ነገሮች፣ [ለ]ስለዘመን ፍጻሜ የሚመለከቱትን ነገሮች፣ ለቤተክርስቲያኔ [ሐ]እገልጥ ዘንድ አላማ አለኝና።

፴፪ እና ለአገልጋዬ ጆሴፍ ይህን ቤት፣ እና በዚህም ክህነትን፣ እና ይህም የሚገ ነባበትን ስፍራ በሚመለከት ሁሉንም ነገ ሮች [ሀ]አሳየዋለሁ።

፴፫ እና ለመገንባት ስታሰላስሉበት በነ በረው ስፍራም ትገነቡታላችሁ፣ እናንተ እንድትገነቡበት የመረጥኩት ስፍራ ነውና።

፴፬ በሙሉ ሀይላችሁ ታገለግሉ ዘንድ፣ ይህም [ሀ]ቅዱስ ይሆን ዘንድ ስፍራውን እቀ ድሰዋለሁ።

፴፭ እና ህዝቤ ድምጼን እና ህዝቤን እን ዲመሩ የመደብኳቸውን [ሀ]የአገልጋዮቼን ድምፅ ቢያደምጡ፣ እነሆ፣ እውነት እላ ችኋለሁ፣ ከስፍራቸውም አይወጡም።

፴፮ ነገር ግን ድምጼን ወይም እነዚህን

፴፬ *ሀ* ት. እና ቃ. ፲፫፡፲፬–፲፮።
ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
፴፭ *ሀ* ኢሳ. ፪፡፫–፮።
፴፮ *ሀ* ቅ.መ.መ. ማጠብ፣
የታጠበ፣ የሚታጠቡ።
፴፯ *ሀ* ዘፀአ. ፳፭፡፭–፱፣ ፴፫፡፯።
ቅ.መ.መ. ታቦት።
ለ ቅ.መ.መ. ቤተመቅደስ፣
የጌታ ቤት።
፴፱ *ሀ* ዘፀአ. ፳፱፡፯።
ቅ.መ.መ. መቀባት።
ለ ቅ.መ.መ. ስነስርዓቶች—
የወኪል ስነስርዓት።
ሐ ት. እና ቃ. ፹፰፡፲፯።
መ ት. እና ቃ. ፲፫፣ ፹፡፱፣
፲፭፡፲፭፡፳፱፣
ጆ.ስ.—ታ. ፭፡፳፱።
ሠ ሕዝ. ፴፭፡፱፣
ት. እና ቃ. ፴፭፡፴፪፣
፹፯፡፳፣ ፲፫፣ ፲፭፡፳፪።
፴፩ *ሀ* ት. እና ቃ. ፲፳፭፡፳፯–፴፪።
ለ ኤፌ. ፩፡፱–፣
ት. እና ቃ. ፳፯፡፣ ፲፫፣
፲፣፪፡፴፡
ሐ ኢ.ኦ. ፩፡፱።
፴፪ *ሀ* ት. እና ቃ. ፣፲፭፡፲፡–፲፯።
፴፫ *ሀ* ቅ.መ.መ. ቅዱስ።
፴፭ *ሀ* ት. እና ቃ. ፩፡፴፣ ፴፣
ቅ.መ.መ. ነቢይ።

የመደብኳቸውን የአገልጋዮቼን ድምፅ ባያ ደምጡ፣ ቅዱስ መሬቴን፣ እና ቅዱስ ስር ዓቶቼን፣ እና ህገ መንግስቴን፣ እና የሰጠ ኋቸውን ቅዱስ ቃላቴን ስለሚያረክሱ አይ ባረኩም።

፴፯ እና እንዲህም ይሆናል በስሜ ቤቴን ብትሰሩ፣ እና ያልኳቸውንም ነገሮች ባታ ደርጉ፣ ለእናንተ የገባሁትን ᵐመሀላ አል ፈፅምም፣ ከእጄም የምትጠብቁትን ቃል ኪዳንም አላሟላም፣ ይላል ጌታ።

፴፰ እናንት በስራችሁ ᵐበረከቶች ሳይ ሆን፣ በሞኝነታችሁና በፊቴ በምታደር ጉት በአጸያፊ ስራዎቻችሁ እርግማንን፣ ቁጣን፣ ንዴትን፣ እና ፍርድን በራሳችሁ ላይ ታመጣላችሁና፣ ይላል ጌታ።

፴፱ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ለስሜ ስራን እንዲሰሩ ለየትኞቹም የሰዎች ልጆች ትእዛዝን ስሰጥ፣ እነዚያም የሰዎች ልጆች ሁሉ በሙሉ ሀይላቸውና ባላቸው ሁሉ ያንን ስራ ቢፈጽሙ፣ እና ᵐቅንነታቸውን ባያጎ ድሉ፣ እና ጠላቶቻቸው ቢመጡባቸው እና ያንንም ስራ እንዳያከናውኑ እንቅፋት ቢሆ ኑባቸው፣ እነሆ፣ ከእነዚያ የሰዎች ልጆች እጆች ላይ ያንንም ስራ በተጨማሪም ᵃላለ መጠየቅ፣ ነገር ግን መስዋዕታቸውን እቀ በል ዘንድ ፍቃዴ ነው።

፴ እና ᵐንስሀ እስካልገቡ እና እስከጠሉኝም ድረስ፣ ክፋትን እና የቅዱስ ህግጋቴን እና ትእዛዛቴን ስራ የሚያደናቅፉትን፣ እስከ ሶስት እና አራት ᵃትውልዶች፣ ᵃእጎበኛ ቸዋለሁ፣ ይላል ጌታ አምላክ።

፴፩ ስለዚህ፣ ᵐበጃክሰን የግዛት ክፍል ሚዙሪ ውስጥ ከተማ እና ᵃቤት በስሜ እን ዲገነቡ ካዘዝኳቸው፣ እና በጠላቶቻቸ ውም ከተደናቀፉት መካከል መስዋዕታቸ ውን የተቀበልኩት በዚህ ምክንያት ነው፣ ይላል ጌታ አምላካችሁ።

፴፪ እና ንስሀ እስካልገቡ እና እስከጠሉኝ ድረስ፣ ᵐፍርድን፣ ቁጣን፣ ንዴትን፣ ልቅ ሶን፣ እና ስቃይን፣ እና ጥርስ ማፏጨትን በራሳቸው ላይ፣ እስከ ሶስት እና አራት ትውልድ እመልስላቸዋለሁ፣ ይላል ጌታ አምላካችሁ።

፴፫ እና እነዚያ ስራ እንዲሰሩ ታዝዘው እና በጠላቶቻቸው እጆች እና በግፍ ተደናቅ ፈው የነበሩትን ሁሉ በሚመለከት ትዕናኑ በት ዘንድ ይህን ለእናንተ ምሳሌ አደርጋ ለሁ፣ ይላል ጌታ አምላካችሁ።

፴፬ እኔ ጌታ አምላካችሁ ነኝና፣ እና በልባ ቸው ᵐንጹህ የሆኑትን፣ እና በሚዙሪ ምድር ውስጥ ᵃየተገደሉትን ወንድሞቻችሁንም አድናለሁ፣ ይላል ጌታ።

፴፭ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ በማ ዝዛችሁ ማንኛቸውም ነገሮች እናንተ ታማኝ መሆናችሁን ለእኔ ᵐታረጋግጡ ዘንድ፣ እና እኔም እባርካችሁ እና በክብር፣ ህያውነት፣ እና በዘለአለማዊ ህይወትንም አጎናጽፋችሁ ዘንድ በስሜ ᵃቤትን እንድትገነቡ፣ በዚህም ስፍራ ይህን ታደርጉ ዘንድ፣ ደግሜ አዛ ችኋለሁ።

፴፮ አሁንም ለእንግዶች ማረፊያ እንድት ገነቡት ያዘዝኳችሁ ማረፊያ ᵐቤትን በሚመ ለከት እላችኋለሁ፣ በስሜም ይሰራ፣ ስሜም በእርሱ ላይ ይሁን፣ እና አገልጋዬ ጆሴፍ እና ቤቱም በዚህ ውስጥ ከትውልድ እስከ ትውልድ ስፍራ ይኑራቸው።

፴፯ ለዚህም ራሱን ቀብቼዋለሁ፣ ከእርሱ በኋላ ያለው ትውልድ የእርሱን በረከት በላ ያቸው ይቀበላሉ።

፴፰ እና ᵐለአብርሐም ስለምድር ነገዶች

፴፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. መሀላ።
፴፰ *ሀ* ዘዳግ. ፭፰፡፲፭።
፴፱ *ሀ* ቅ.መ.መ. ትጋት።
ለ ት.እና ቃ. ፶፯፡፱፡ ፲ሸ፶፯፡፱።
፴ *ሀ* ቅ.መ.መ. መጸጸት፣ ንስሀ መግባት።
ለ ዘዳግ. ፭፡፱፣ ት.እና ቃ. ፶፰፡፴፯–፴፯።
ሐ ሞዛያ ፲፪፡፭።
፴፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. የጃክሰን አውራጃ፣ ምዙሪ (ዮኤስኤ)።
ለ ት.እና ቃ. ፲፲፫፡፲፭።
፴፪ *ሀ* ት.እና ቃ. ፲፯፭፡፲፭–፳፫።
፴፫ *ሀ* ቅ.መ.መ. ንጹህ፣ ንጹህነት።
ለ ት.እና ቃ. ፶፰፡፲፫፣ ፲፫፡ ፳፯–፳፰።
፴፭ *ሀ* አብር. ፫፡፳፭።
ለ ት.እና ቃ. ፲፯፭፡፱።
፴፮ *ሀ* ት.እና ቃ. ፲፯፭፡፳ሸ–፳፰።
፴፯ *ሀ* ዘፍጥ. ፲፪፡፫፣ ፳፪፡፲፰፣ አብር. ፪፡፲፭። ቅ.መ.መ. አብርሐም።

እንዳልኩትም፣ ለአገልጋዬ ጆሴፍም እን ዲሁም እለዋለሁ፥ በአንተ እና ^በዘርህ የም ድር ነገዶች ይባረካሉ።

፶፱ ስለዚህ፣ አገልጋዬ ጆሴፍ እና ከእ ርሱም በኋላ ዘሮቹ በዚያ ቤት ከትውልድ እስከ ትውልድ፣ ለዘለአለም ስፍራ ይኑራ ቸው፣ ይላል ጌታ።

፷ የቤቱም ስም የናቩ ቤት በመባል ይታ ወቅ፤ እና ለሰውም የሚያስደስት መኖሪያ እና የፅዮንን ክብር እና የዚህ የማዕዘን ድን ጋይ ክብርን ያሰላስል ዘንድ ለደከመውም ተጓዢ ማረፊያ ስፍራ ይሁን፤

፷፩ እንደዝነኛ ^አትክልት እና እንደ ^ጠባቂዎች በግድግዳዋ ላይ ካስቀመጥኳ ቸው ምክር ደግሞም ይቀበል ዘንድ።

፷፪ እነሆ፣ እውነት እላችኋለሁ፣ አገል ጋዬ ጆርገ ሚለር እና አገልጋዬ ላይመን ዌይት፣ እና አገልጋዬ ጆን ስናይደር፣ እና አገልጋዬ ፒተር ሀውስ ራሳቸውን ያደራጁ እና ቤቱን ለመገንባትም ባላቸው አላማም በመካከላቸው አንዱን እንደ ቡድናቸው ፕሬዘደንት ይመድቡ።

፷፫ እና እነርሱም ያን ቤት ለመስራትም ሸቀጥ የሚቀበሉበት ህገ መንግስትን ይመ ስርቱ።

፷፬ እና በዚያ ቤት ውስጥ የድርሻቸውን ሸቀጥ ከሀምሳ ዶላር በላይ አይቀበሉ፣ እና ለዚያ ቤት ሸቀጥም ከእያንዳንዱ ሰው አስራ አምስት ሺህ ዶላሮች እንዲቀበሉ ይፈቀ ድላቸው።

፷፭ ነገር ግን ከማንም አንድ ሰው ከአ ስራ አምስት ሺህ ዶላሮች በላይ እንዲቀ በሉ አይፈቀድላቸውም።

፷፮ እና ከማንም ሰው ለዚያ ቤት ሸቀጥ የድርሻውን ከአስራ አምስት ሺህ ዶላሮች በታች እንዲቀበሉ አይፈቀድላ ቸውም።

፷፯ እና ሸቀጡን በሚቀበልበት ጊዜ ለሸቀጡ ካልከፈለ በስተቀር፣ ማንንም ሰው እንደዚህ ቤት ሸቀጥ ድርሻ ያዥ ለመቀበል አይፈቀድላቸውም።

፷፰ በእጆቻቸው በሚከፍለው የሸቀጡ ክፍያው በዚያ ቤት ውስጥ ሸቀጥን ይቀ በል፤ ነገር ግን በእጆቻቸው ምንም ካልከ ፈለ በእዚያ ቤት ውስጥ ምንም ሸቀጥ አይ ቀበል።

፷፱ እና ማንም ሸቀጥን በእጆቻቸው ቢከፈል በቤቱ ውስጥ እና ለእርሱና ከእ ርሱ በኋላ ለመጡት ትውልዶችም፣ ከት ውልድ እስከትውልድ፣ እርሱ እና የእ ርሱ ወራሾች ሸቀጡን እስከያዙ ድረስ እና በራሳቸው ነጻ ፈቃድ ወይም ስራ ሸቀጡን ከእጆቻቸው አውጥቶ ካላስተላለፈ ወይም ካልሸጠው በስተቀር፣ ፈቃዴን ብታደርጉ ለሸቀጥ ይሆንለታል፣ ይላል ጌታ አምላ ካችሁ።

፹ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ አገ ልጋዬ ጆርጀ ሚለር እና አገልጋዬ ላይመን ዋይት እና አገልጋዬ ጆን ስናይደር፣ እና አገልጋዬ ፒተር ሀውስ በገንዘቦች ወይም የእውነት ዋጋ ያለው ገንዘብ በሚቀበሉበት ንብረቶች ምንም ሸቀጥ በእጆቻቸው ቢቀ በሉ፣ በቤቱ ውስጥ እንጂ ያንን ሸቀጥ የት ኛውንም ክፍል ለምንም አላማ አይመድቡ።

፹፩ እና ከቤቱ ላይ በስተቀር የሸቀጡን ማንኛውንም ክፍል በሌላ ስፍራ ሸቀጡን ከያዙት ሳይፈቅዱ ከመደቡት እና በየት ኛውም ስፍራ የመደቡትን ሸቀጥ በአራት እጥፍ መልሰው ባይከፍሉ፣ ይረገማሉ፣ እና ከስፍራቸውም ይወጣሉ፣ ይላል ጌታ አም ላክ፤ እኔ ጌታ አምላካችሁ ነኝ እና በእነዚህ በማንኛቸውም ነገሮች ^አይዘበትብኝምና።

፹፪ እውነት እላችኋለሁ፣ አገልጋዬ ጆሴፍ፣ መልካም እንደሚመስለው፣ ቤቱ ከመገንባቱ በፊት ለሸቀጡ በእጆቻ ቸው ይክፈል፤ ነገር ግን አገልጋዬ ጆሴፍ ለዚያ ቤት ሸቀጥ ከአስራ አምስት ሺህ በላይ ወይም ከአምስት ሺህ በታች መክፈል አይ

፶፯ ለ ት. እና ቃ. ፲፫፡ ፲፪።
ቅ.መ.መ. የአብርሐም ቃል ኪዳን።

፷፭ ሀ ኢሳ. ፷፭፡ ፫፤ ሕዝ. ፴፬፡ ፳፱።
ለ ቅ.መ.መ. መጠበቅ፣ ጠባቂ።

፹፯ ሀ ገላ. ፮፡ ፯።

ችልም፤ ወይም ሌላም ሰው ይህን ማድረግ አይችልም፣ ይላል ጌታ።

፳፫ እና ፈቃዴን ለማወቅ ፈቃድ ያላቸው ሌሎችም አሉ፣ ከእጆቼ ጠይቀውታልና።

፳፬ ስለዚህ፣ ስለአገልጋዬ ቪንሰን ናይት እላችኋለሁ፣ ፈቃዴን ቢያደርግ በዚያ ቤት ላይ ለራሱ እና ከእርሱ በኋላ ለሚመጡ ትውልዶቹ፣ ከትውልድ እስከ ትውልድ ሽቀጥን ያስገባ።

፳፭ እና በህዝብ መካከል፣ የድሆች እና እርዳታን ለሚሹ [a]ለመለመን፣ ድምጹን ረጅም እና ጉልህ በማድረግ ያንሳ፤ አይ ውደቅ፣ ወይም ልቡም ተስፋ አይቁረጥ፤ እና መስዋዕቶቹን [b]እቀበላቸዋለሁ፣ እንደ ቃየን መስዋእቶች አይደሉምና፣ እርሱም የእኔ ይሆናልና፣ ይላል ጌታ።

፳፮ ቤተሰቡም ይደሰቱ እና ከስቃይም ልባቸውን ይመልሱ፤ እኔ መርጨው እና ቀብቼዋለሁና፣ እና በቤቱም መካከልም ይከብራል፣ ለኃጢአቶቹ ሁሉ ምህረትን እሰጠዋለሁና፣ ይላል ጌታ። አሜን።

፳፯ እውነት እላችኋለሁ፣ አገልጋዬ ሀይረም ስሚዝ ለእራሱ እና ከእርሱ በኋላ ለሚመጡት ትውልዶች፣ ከትውልድ እስከ ትውልድ፣ መልካም እንደሚመስ ለው በቤቱ ላይ ሽቀጥን ያስቀምጥ።

፳፰ አገልጋዬ አይዛክ ጋላንድ በቤቱ ላይ ሽቀጥ ያስገባ፤ እኔ ጌታ ለሰራው ስራም እወደዋለሁና እና ለኃጢአቶቹ በሙሉ ምህረትን እሰጠዋለሁና፤ ስለዚህ፣ በዚ ህም ቤት ውስጥ ሽቀጥ እንዳለውም ከት ውልድ እስከ ትውልድ ይታወስ።

፳፱ አገልጋዬ አይዛክ ጋለንድም በመካከ ላችሁ ይመደብ፣ እና ከአገልጋዬ ሀይረም ስሚዝ ጋር አገልጋዬ ጆሴፍ የሚጠቁምላ ቸውን ስራ ለማከናወን በአገልጋዬ ዊልያም ማርክስም ይሾም፣ እና በእርሱም ይባረክ፣ እና እነርሱም በታላቅ በረከትም ይባረካሉ።

፴ አገልጋዬ ውልያም ማርክስም መል ካም እንደሚመስለው ለራሱ እና ለትው ልዱ፣ ከትውልድ እስከ ትውልድ፣ በቤቱ ላይ ለሽቀጥ ይክፈል።

፴፩ አገልጋዬ ሄንሪ ጂ ሸርውድ መልካም እንደሚመስለው ለራሱ እና ከእርሱ በኋላ ለዘሩ፣ ከትውልድ እስከ ትውልድ፣ በቤቱ ላይ ለሽቀጥ ይክፈል።

፴፪ አገልጋዬ ውልያም ሎው መልካም እንደሚመስለው ለራሱ እና ከእርሱ በኋላ ለዘሩ፣ ከትውልድ እስከ ትውልድ፣ በቤቱ ላይ ለሽቀጥ ይክፈል።

፴፫ ፈቃዴን የሚያደርግ ቢሆን፣ ቤተሰ ቡን ወደ ምስራቅ ምድር፣ እንዲሁም ወደ ከርትላንድ አይውሰድ፤ ይህ ቢሆን፣ እኔ ጌታ ከርትላድን እገነባለሁ፣ እና እኔ ጌታ በዚያ ለሚኖሩትም የሚመቱበትን ጅራፍ አዘጋጅቼላቸዋለሁ።

፴፬ እና ከአገልጋዬ አልሞን ባቢት ያልተ ደሰትኩበት ብዙ ነገሮች አሉ፤ እነሆ፣ ከመ ደብኩለት ምክር፣ እንዲሁም ከቤተክርስ ቲያኔ አመራር በላይ የእራሱን ምክር ለመ መስረት ተነሳስቷል፤ እና ህዝቤም ያመል ኩት ዘንድ [c]የወርቅ ጥጃን ያቆማል።

፴፭ ትእዛዛቴን በመሻት የመጣ ማንም ሰው ከዚህ ስፍራ [d]አይሂድ።

፴፮ እዚህም የሚኖሩ ቢሆን፣ በእኔ ይኑሩ፤ እና ቢሞቱም፣ በእኔ ይሙቱ፤ ከስራዎቻቸው ሁሉ በዚህ [e]ያርፋሉና፣ እና ስራዎቻቸውንም ይቀጥላሉና።

፴፯ ስለዚህ፣ አገልጋዬ ውልያም እም ነቱን በእኔ ላይ ያድርግ፣ እና በምድሩ ላይ ባለው ህመም ምክንያትም ስለቤተ ሰቡ መፍራቱን ያቁም። [f]ብትወዱኝ ትእ ዛዛቴን ጠብቁ፤ እና የምድሩም ህመም ለክ ብራችሁ [g]ይቀየራል።

፴፰ አገልጋዬ ውልያም ይሂድ እና በጎላ ድምፅም እና በታላቅ ደስታ፣ [h]በመንፈሴም

፳፭ *ሀ* ምሳ. ፴፩፡ ፱።
ለ ዘፍጥ. ፬፡ ፬–፭፤ ሙሴ ፭፡ ፲፰–፳፰።
፴፬ *ሀ* ዘፀአ. ፴፪፡ ፪–፬።
፴፭ *ሀ* ሉቃ. ፱፡ ፳፪።
፴፮ *ሀ* ራዕ. ፲፬፡ ፲፫። ቅ.መ.መ. እረፍት፤ ገነት።
፴፯ *ሀ* ዮሐ. ፲፬፡ ፲፭።
ለ ት. እና ቃ. ፻፳፭፡ ፳፣ ፻፳፡ ፯።
፴፰ *ሀ* ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ—እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ።

እንደተነሳሳ፣ ዘለአለማዊውን ወንጌሌን ለዋርሶ ነዋሪዎች፣ እና ደግሞም ለካርቴጅ ነዋሪዎች፣ እና ደግሞም ለበርሊንግተን ነዋሪዎች፣ እና ደግሞም ለማድሰን ነዋሪዎች፣ ያውጅ፣ እና በትእግስትና በቅንነት በአጠቃላይ ጉባኤ ላይ መመሪያን ይጠብቅ፣ ይላል ጌታ።

፲፱ ፈቃዴን የሚያደርግ ቢሆን፣ የአገልጋዬ ጆሴፍን ምክር ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ያድምጥ፣ በችሎታውም [ሀ]ድሆችን ይርዳ፣ እና ለምድርም ነዋሪዎች ቅዱስ ቃሌን [ለ]አዲስ ትርጉም ያውጅ።

፲፩ እና ይህንንም ቢያደርግ በሚበዙ በረከቶች [ሐ]እባርከዋለሁ፣ እርሱ አይተውም፣ ወይም ዘሩም ዳቦ [መ]እየለመኑ አይገኙም።

፲፪ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ አገልጋዬ ሀይረም በአባቱ እና በበረከት፣ እና ደግሞም በመብት የተመደበለትን ክህነት እና [ሠ]የፓትሪያርክ ሀላፊነት ይወስድ ዘንድ፣ አገልጋዬ ውልያም በአገልጋዬ ሀይረም ምትክ ለአገልጋዬ ጆሴፍ አማካሪ እንዲሆን ይመደብ፣ ይሾም፣ እናም ይቀባ፤

፲፫ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በህዝቤ ሁሉ ላይ [ረ]የፓትሪያርክ በረከት ቁልፎችን ይያዝ፣

፲፫ ማንም እርሱም የሚባርክ ይባረካል፣ እና ማንም የሚረግመውም [ሰ]ይረገማል፤ በምድር [ሸ]የሚያስረው ሁሉ በሰማያት የታሰረ ይሆናል፣ በምድርም የሚፈታው ሁሉ በሰማያት የተፈታ ይሆናል።

፲፬ እና ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ለአገልጋዬ ጆሴፍ ለቤተክርስቲያኔ ነቢይ፣ [ቀ]ባለራዕይ፣ እናም ገላጭ እንዲሆን መድቤዋለሁ፤

፲፭ ከአገልጋዬ ጆሴፍ ጋር በአንድነት ይሰራም ዘንድ፤ እና የሚጠይቀውን እና የሚቀበልበትን [በ]ቁልፎች የሚያሳየውን የአገልጋዬን የጆሴፍን ምክር ይቀበል፣ እና በዚህም አይነት በረከት፣ እና አገልጋዬ በነበረው [ተ]ኦሊቨር ካውድሪ ላይ ተጭኖ የነበረውን ግርማ፣ እና ክብር፣ እና ክህነት፣ እና የክህነት ስጦታም ይጎናጸፋል፤

፲፮ አገልጋዬ ሀይረምም ስለማሳየው ነገሮች ምስክነትን ይሰጥ ዘንድ፣ ስሙም በክብር ማስታወሻ ከትውልድ እስከ ትውልድ፣ ለዘለአለም ይሆን ዘንድ መድቤዋለሁ።

፲፯ አገልጋዬ ውልያም ሎውም በረከቶችን በመጠየቅ የሚቀበልበትን ቁልፎች ይቀበል፤ በፊቴም [ቸ]ትሁት፣ እና [ኀ]ያለ ነቀፋም ይሁን፣ እና የሁሉንም ነገር እውነትነት የሚገልፅ፣ እና በዚያችም ሰዓት እንዴት እንዲናገር የሚሰጠው መንፈሴን፣ እንዲሁም [ነ]አፅናኝን ይቀበል።

፲፰ እና እነዚህም [ኘ]ምልክቶች ይከተሉታል—የታመሙትን [አ]ይፈውሳል፣ አጋንንትን ያወጣል፣ ገዳይ መርዝንም ከሚሰጡትም ከእነርሱም ይድናል፤

፲፱ እና [ከ]መርዛማም እባብ ተረከዙን በማይነክስበት መንገድ ይመራል፣ እና በሀሳቡም [ወ]አይነ ህሊናው የንስር ክንፍ እንደሚበር ወደላይ ይብረር።

፲ እና የሞተውን እንዲያነሳ ብፈቅድ፣ ድምጹን አይሰብስብ።

፲፩ ስለዚህ፣ አገልጋዬ ውልያምም በደስታ እና በሀሴት በዙፋኑ ላይ ለዘለአለም ለተቀመጠው ሆሳዕና በማለት፣ በታላቅ ድምጽ ይጩህ እናም አይከልከል፣ ይላል ጌታ አምላክህ።

፲፪ እነሆ፣ እላችኋለሁ፣ ለአገልጋዬ ውልያም እና ለአገልጋዬ ሀይረም፣ እና ለእርሱም

፲፱ [ሀ] ት. እና ቃ. ፫፯፡፫።
[ለ] ይህም የጆሴፍ ስሚዝ የመፅሐፍ ቅዱስ ትርጉም ማለት ነው።
፲ [ሀ] ቅ.መ.መ. መባረክ፣ የተባረከ፣ በረከት።
[ለ] መዝ. ፴፯፡ ፳፭።
፲፩ [ሀ] ት. እና ቃ. ፲፯፡ ፴፱–፴።
ቅ.መ.መ. የአባቶች አለቃ፣ ፓትሪያርክ።
፲፪ [ሀ] ቅ.መ.መ. የፓትሪያርክ በረከቶች።
፲፫ [ሀ] ት. እና ቃ. ፲፴፪፡ ፴፭–፴፯።
[ለ] ማቴ. ፲፮፡ ፲፱።
ቅ.መ.መ. ማተም፣ ማስተሳሰር።
፲፬ [ሀ] ት. እና ቃ. ፲፯፡ ፲፭–፲፪።
ቅ.መ.መ. ባለራዕይ።
፲፭ [ሀ] ት. እና ቃ. ፮፡ ፳፫።
[ለ] ቅ.መ.መ. ካውደሪ፣ ኦልቨር።
፲፮ [ሀ] ቅ.መ.መ. ትሁት፣ ትሕትና።
[ለ] ቅ.መ.መ. ተንኮል።
[ሐ] ቅ.መ.መ. አፅናኝ።
፲፰ [ሀ] ማር. ፲፮፡ ፲፯–፲፰።
ቅ.መ.መ. የመንፈስ ስጦታዎች።
[ለ] ቅ.መ.መ. መፈወስ፣ ፈውሶች።
፲፱ [ሀ] ት. እና ቃ. ፲፰፡ ፫፯–፫፲።
[ለ] ዘፀአ. ፲፱፡ ፱፣ ኢሳ. ፶፡ ፴፭።

ብቻ ተልዕኮን አዘጋጅቼላቸዋለሁ፤ እና አገ
ልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝም በቤት ይቆይ፣ ይፈ
ለጋልና። የሚቀረውን ከዚህ በኋላ አሳያች
ኋለሁ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

፪፫ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ አገ
ልጋዬ ᵐስድኒ ቢያገለግለኝ እና ለአገልጋዬ
ጆሴፍ ስሚዝ አማካሪ ቢሆን፣ ይነሳ እና
ወደፊትም ይምጣ እና በተጠራበት ሀላፊ
ነትም ይቁም፣ እና በፊቴም ትሁት ይሁን።

፪፬ እና ተቀባይነት ያለውን መስዋዕትና
እውቀትን ቢያቀርብልኝ፣ እና ከህዝቤም
ጋር ቢቆይ፣ እነሆ እኔ ጌታ አምላክህ የሚ
ፈወሰውን እፈውሳለሁ፤ እና በተራሮችም
ላይ ድምጹን ከፍ ያደርጋል፣ እና በፊቴም
ᵐየሚናገርልኝ ይሆናል።

፪፭ ይምጣ እና አገልጋዬ ጆሴፍ በሚኖ
ርበት አካባቢም ቤተሰቡንም በዚያ ያኑር።

፪፮ እና በጉዞዎቹም ሁሉ እንደመለከት
ድምጽ ድምጹን ከፍ ያድርግ፣ እና የም
ድር ነዋሪዎችንም ስለሚመጣው ከሚመ
ጣው ቍጣ እንዲሸሹ ያስጠንቅቃቸው።

፪፯ አገልጋዬ ጆሴፍን ይርዳ፣ እና አገል
ጋዬ ውልያም ሎውም ከዚህ በፊት እንዳ
ልኳችሁ ለምድር ነገስታት የክብር ᵐአዋጅን
በማድረግ አገልጋዬ ጆሴፍን ይርዳ።

፪፰ አገልጋዬ ስድኒ ፈቃዴን ቢያደርግ፣
ቤተሰቡን ወደ ᵐምስራቅ ምድር አይውሰ
ዳቸው፣ ነገር ግን እንዳልኩት መኖሪያቸ
ውን ይቀይር።

፪፱ እነሆ፣ ለእናንተ ከመደብኩላችሁ
ከተማ፣ እንዲሁም ᵐከናቩ ከተማ፣ ውጪ
ደህንነትን እና መሸሸጊያን ለማግኘት
መሻቱ ፍቃዴ አይደለም።

፪፲ እውነት እላችኋለሁ፣ አሁንም
ድምጼን ብታደምጡ፣ መልካም ይሆንላ
ችኋል። እንዲህም ይሁን። አሜን።

፪፲፩ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ አገ
ልጋዬ ኤመስ ዴቪስ የማረፊያ ቤት፣ እን
ዲሁም የናቩን ቤት፣ እንዲገነቡ ለመደብ
ኳቸው ሰዎች በእጆቻቸው ላይ ሽቀጥ ይክ
ፈል።

፪፲፪ ፍላጎቱም ቢሆን ይህንን ያድርግ፤
እና የአገልጋዬ ጆሴፍን ምክር ያድምጥ፣
እና የሰዎችንም እምነት ያገኝ ዘንድ በእ
ጆቹ ይስራ።

፪፲፫ እና እንዲንከባከባቸው በተሰጡት
ነገሮች ሁሉ፣ አዎን እንዲሁም በጥቃቅን
ነገሮች፣ ታማኝ እንደሆነ ራሱን ሲያረጋ
ግጥ፣ በብዙ ነገሮች ᵐአስተዳዳሪ ይሆናል።

፪፲፬ ስለዚህ፣ የላቀ ክብር ይኖረውም
ዘንድ እራሱን ᵐያዋርድ። እንዲህም ይሁን።
አሜን።

፪፲፭ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣
አገልጋዬ ሮበርት ዲ ፎስተር ድምጼን ቢታ
ዘዝ፣ ከእርሱ ጋርም በገባው ስምምነት መሰ
ረት ለአገልጋዬ ጆሴፍ ቤት ይስራ፣ ከጊዜ
ወደጊዜም በሮች ይከፈቱለታልና።

፪፲፮ እና ለሞኝነት ስራውም ንስሀ ይግባ፣
እና ᵐበልግስና እራሱን ያልብስ፤ እና ክፉ
ማድረግንም ያቁም፣ እና የክፉ ንግግሮቹ
ንም ያቁም።

፪፲፯ እና ከትውልድ ወደ ትውልድ፣
ለራሱ እና ከእርሱ በኋላ ለሚመጡት
ትውልዶች፣ ለናቩ ቤት ቡድኖችም ሽቀ
ጥን ይክፈል፤

፪፲፰ እና አገልጋዮቼን የጆሴፍን፣ እና
ሀይረምን፣ እና የውልያም ሎው፣ እና የፅዮ
ንንም መሰረት ይገነቡ ዘንድ የጠራኋቸውን
ባለስልጣናት ምክሮችንም ያድምጥ፤ እና
ለዘለአለም መልካም ይሆንለታል። እንዲ
ህም ይሁን። አሜን።

፪፲፱ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣
በመፅሐፈ ሞርሞን፣ እና በሰጠኋችሁ ራዕ
ዮች የሚያምን ካልሆነ በስተቀር ማንም ሰው
ለናቩ ቤት ቡድኖች ሽቀጥን አይክፈል፣
ይላል ጌታ አምላካችሁ፤

፪፫ ᵐ ቅ.መ.መ. ሪግደን፣ ስድኒ።
፪፬ ᵐ ዘፀአ. ፬፡ ፲፱–፲፯፣
፪ ኔፊ ፫፡ ፲፯–፲፰፣
ት. እና ቃ. ፫፡ ፱–፲፩።
፪፯ ᵐ ት. እና ቃ. ፪፳፬፡ ፪–፬።
፪፰ ᵐ ት. እና ቃ. ፪፳፬፡ ፲፪–፲፫።
፪፱ ᵐ ቅ.መ.መ. ናቩ፣ ኢሊኖይ
(ዮ.ኤስ.ኤ.)።
፪፲፫ ᵐ ማቴ. ፳፭፡ ፲፬–፴።
፪፲፬ ᵐ ማቴ. ፳፫፡ ፲፪፣
ት. እና ቃ. ፲፭፡ ፵፪።
፪፲፯ ᵐ ቁላ. ፫፡ ፲፬።
ቅ.መ.መ. ልግስና።

፤፳፭ ከእነዚህም ᐸየበዛ ወይም ያነሰ ከክፉው የሚመጣ ነውና፣ እና በበረከ ቶች ሳይሆን እርግማኖች ይከተሏቸዋ ልና፣ ይላል ጌታ አምላካችሁ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

፤፳፭፤ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ የናቩ ቤት ቡድኖች የናቩ ቤትን ለመገን ባት ለሚያደርጉት አገልግሎታቸው ሁሉ በቂ ደመወዝ ይከፈላቸው፤ እና ደሞዛች ውም፣ ስለዋጋው በሚመለከት፣ በመካከ ላቸው የሚስማሙበት ይሁን።

፤፳፭፤ እና እያንዳንዱ ሽቀጥን የሚከፍለ ውም የድርሻ ደሞዙን፣ አስፈላጊም ከሆነ የሚደገፉበትን ይክፈል፣ ይላል ጌታ፤ አለ በለዚያም፣ አገልግሎታቸው በዚያ ቤት እንደ ሽቀጥ ይቆጠርላቸዋል። እንዲህም ይሁን። አሜን።

፤፳፭፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ለእናንተ ለክ ህነት ስልጣኔ አባል ለሆናችሁት ᐸባለስልጣ ናት፣ ᐹቁልፎቹንም ትይዙ ዘንድ፣ እንዲ ሁም በአንድያ ልጅ ስርዓት የሆነውን ᐹየመ ልክ ጴጴቅን ስርዓት ክህነት አሁን እሰጣ ችኋለሁ።

፤፳፭፤ መጀመሪያ፣ ሀይረም ስሚዝን ለእና ንተ ᐸፓትሪያርክ እንዲሆን፣ የሚመጡባች ሁን፣ የፈተና ᐹሰአታትን በመቋቋም እንዳ ትወድቁ ለቤዛም ቀን ᐹየምትታተሙባች ውን የቤተክርስቲያኔን ᐸማስተሳሰሪያ በረ ከቶችን፣ እንዲሁም ቅዱስ ᐸየተስፋ መን ፈስን እንዲይዝ እሰጠዋለሁ።

፤፳፭፤ አገልጋዬ ጆሴፍ በቤተክርስቲ ያኔ ሁሉ አስተዳዳሪ ሽማግሌ፣ ተርጓሚ፣ ᐸገላጭ፣ ባለራዕይ፣ እና ነቢይ እንዲሆን እሰጣችኋለሁ።

፤፳፭፤ ለእርሱም አገልጋዬን ስድኒ ሪግደንን እና አገልጋዬን ውልያም ሎውን እንደ አማ ካሪዎቹ እሰጠዋለሁ፣ እነዚህም ለቤተክር ስቲያኗ ᐸየእግዚአብሔርን ቃላት ለመቀበል ቡድንን እና ቀዳሚ አመራርን ያቋቁማሉ።

፤፳፭፤ አገልጋዬ ᐸብሪገም ያንግን የአስራ ሑለቱ ተጓዥ ሽንጎ ፕሬዘደንት እንዲሆን እሰጣችኋለሁ፤

፤፳፭፤ ᐸአስራ ሁለቱም በምድር አራቱ ማዕዘናት ላይ የመንግስቴን ስልጣን ለመ ክፈት፣ እና ከዚያም በኋላ ቃሌን ለሁሉም ፍጥረቶች ᐹይልኩ ዘንድ ቁልፎችን ይዘ ዋል።

፤፳፭፤ እነዚህም ሂበር ሲ ኪምባል፣ ፓርሊ ፒ ፕራት፣ ኦርሰን ፕራት፣ ኦርሰን ሀይድ፣ ውልያም ስሚዝ፣ ጆን ቴይለር፣ ጆን ኢ ፔጅ፣ ዊልፈርድ ዉድረፍ፣ ዊለርድ ርቻር ድስ፣ ጆርጅ ኤ ስሚዝ ናቸው፤

፤፳፭ ᐸዴቪድ ፓትንን ወደ እኔም ዘንድ ᐹወስጄዋለሁ፤ እነሆ፣ የእርሱን ክህነት ማንም ሰው አይወስድበትም፤ ነገር ግን፣ እውነት እላችኋለሁ፣ በዚያ ጥሪ ሌላ ሊመ ደብ ይቻላል።

፤፳፭፤ ደግሞም፣ እላችኋለሁ፣ ለፅዮን የማእዘን ራስ ድንጋይ እንዲሆን ᐸከፍተኛ ሽንጎን ሰጠኋችሁ—

፤፳፭፤ በስምም፣ ሳሙኤል ቤንት፣ ሔንሪ ጂ ሽርውድ፣ ጆርጅ ደብሊው ሀሪስ፣ ቻርልስ ሲ ሪች፣ ቶማስ ግሮቨር፣ ኒወል ኒይት፣ ዴቪድ ዶርት፣ ዱንባር ዊልሰን— ሲሞር ብረንሰንን ወደ እኔ ወስጃለሁ፤ የእርሱን ክህነት ማንም ሰው አይወስድ በትም፤ ነገር ግን በዚያ ክህነት ስልጣን ላይ ሌላ በእርሱ ምትክ ሊመደብ ይቻ ላል፣ እና እውነት እላችኋለሁ፣ አገል ጋዬ አሮን ጆንሰን በእርሱ ምትክ ለዚህ

፤፳፭ ሀ ማቴ. ፭፡፴፯፤ ት. እና ቃ. ፶፰፡፯።
፤፳፭፣ ሀ ቅ.መ.መ. ሀላፊነት፣ ሀላፊ። ለ ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች። ሐ ቅ.መ.መ. የመልክ ጴጴቅ ክህነት።
፤፳፭፤ ሀ ቅ.መ.መ. የአባቶች አለቃ፣ ፓትሪያርክ። ለ ራዕ. ፫፡፲፤ ሐ ኤፌ. ፬፡፴፤ መ ቅ.መ.መ. ማተም፣ ማስተሳሰር። ሠ ት. እና ቃ. ፫፲፯፡፶፣ ፹፰፡፫–፴። ቅ.መ.መ. ቅዱስ የተስፋ መንፈስ።
፤፳፭፭ ሀ ት. እና ቃ. ፳፩፡፭። ቅ.መ.መ. ባለራዕይ።
፤፳፭፯ ሀ ት. እና ቃ. ፯፡፬–፭።
፤፳፭፯ ሀ ቅ.መ.መ. ያንግ፣ ብሪገም።
፤፳፭፰ ሀ ቅ.መ.መ. ሐዋሪያ። ለ ማር. ፲፮፡፲፭።
፤፳፭ ሀ ቅ.መ.መ. ፓተን፣ ዴቪድ ደብሊው። ለ ት. እና ቃ. ፤፳፭፡፲፱።
፤፳፭፭ ሀ ቅ.መ.መ. ከፍተኛ ሽንጎ።

ጥሪ ይሾም—ዴቪድ ፋልመር፣ አልፊየስ ከትለር፣ ውልያም ሀንቲንግተን።

፲፱ ደግሞም፣ ዶን ሲ ስሚዝን በሊቀ ካህናት ቡድን ላይ ፕሬዘደንት እንዲሆን እሰጣችኋለሁ፤

፲፳ ይህም ስርዓት የማይጓዙ ፕሬዘደንቶች ወይም በውጪ በተበተኑት በተለያዩ ᵐካስማዎች አገልጋዮች እንዲሆኑ የተመደቡ ብቁ ለሚሆኑበት አላማ የተመሰረተ ነው፤

፲፳፩ እና ቢፈለጉም መጓዝ ይችላሉ፣ ነገር ግን በአንድ ስፍራ እንደሚያገለግሉ ፕሬዘደንቶች ይሾሙ፤ ይህም የጥሪአቸው ሀላፊነት ነው፣ ይላል ጌታ አመላካችሁ።

፲፳፪ በቤተክርስቲያኔ ሊቀ ካህናት ቡድኖችን ያስተዳድሩ ዘንድ አማሳ ላይማንን እና ኖዋ ፓከርድን እንደአማካሪዎቹ እሰጠዋለሁ፣ ይላል ጌታ።

፲፳፫ ደግሞም፣ እላችኋለሁ፣ የክህነት ስልጣናቸው ᵐየሽማግሌዎች ቡድኖችን እንዲያስተዳድሩ የሆነውን ጆን ኤ ሂክስን፣ ሳሙኤል ዊልያምስን፣ እና ጀሲ ቤከርን እሰጣችኋለሁ፣ ያም ቡድን የተመሰረተው ለማይጓዙ አገልጋዮች ነው፤ ይህም ቢሆን መጓዝ ይችላሉ፣ ነገር ግን የተሾሙት በቤተክርስቲያኗ የማይጓዙ አገልጋዮች እንዲሆኑ ነው፣ ይላል ጌታ።

፲፳፬ ደግሞም፣ ጆሴፍ ያንግን፣ ጆሳያ በተርፊእልድን፣ ዳንኤል ማይልስን፣ ሄንሪ ሀሪማንን፣ ዜራ ፑልሲፈርን፣ ሊቫይ ሀንኮክን፣ ጄምስ ፎስተርን ᵐየሰባዎቹን ቡድን እንዲያስተዳድሩ እሰጣችኋለሁ።

፲፳፭ ይህም ቡድን የተመሰረተው የሚጓዙ ሽማግሌዎች በአለም ሁሉ፣ የሚጓዙ ከፍተኛ ሸንጎ፣ ሐዋሪያቴ በፊቴ መንገዶችን ለማዘጋጀት በሚልኳቸው በማናቸውም ስፍራዎች ስለ ስሜ እንዲመሰክሩ ነው።

፲፳፮ በዚህ ቡድን እና በሽማግሌዎች ቡድን ልዩነት ቢኖር አንዱ ዘወትር ይጓዛል እና ሌላው በቤተክርስቲያኔ ላይ ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲያስተዳድር ነው፤ አንዱ ከጊዜ ወደ ጊዜ የማስተዳደር ሀላፊነት አለው፣ እና ሌላውም የማስተዳደር ምንም ሀላፊነት የለውም፣ ይላል ጌታ አምላካችሁ።

፲፳፯ ደግሞም፣ እላችኋለሁ፣ ቪንሰን ናይትን፣ ሳሙኤል ኤች ስሚዝን፣ እና የሚቀበለው ቢሆን ሻድራክ ራውንዲን የኤጲስ ቆጶስ አመራርን እንዲያስተዳድር እሰጣችኋለሁ፤ የዚህ ᵐኤጲስ ቆጶስ አመራር እውቀት ᵃበትምህርት እና ቃል ኪዳኖች መፅሀፍ ውስጥ ተሰጥቷችኋል።

፲፳፰ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ሳሙኤል ሮልፍ እና አማካሪዎቹ እንደ ቁሶቹ ፕሬዘደንት፣ እና የመምህራን ፕሬዘደንት እና አማካሪዎች፣ እና ደግሞም የዲያቆናት ፕሬዘደንትና አማካሪዎች፣ እና ደግሞም የካስማ ፕሬዘደንቶችና አማካሪዎች እንዲሆኑ እሰጣችኋለሁ።

፲፳፱ የበላይ ሀላፊዎችን እና እነዚህን ቁልፎች ለእርዳታ እና ለማስተዳደር፣ ለአገልግሎቱ ስራዎችና ለቅዱሳኔ ᵐፍጹምነት ሰጥቻችኋለሁ።

፲፳፲ እና እነዚህን ሀላፊነቶች በሙሉ እና የጠቀስኳቸውን ስሞች በአጠቃላይ ጉባኤዬም ላይ ᵐታሟሏቸው እና ታጸድቋቸው ዘንድ ትእዛዝን እሰጣችኋለሁ፣ አለበለዚያም በአጠቃላይ ጉባኤዬም ላይ አታፅድቋቸውም።

፲፳፲፩ እና በቤቴ ውስጥም ለስሜ ስትገነቡት ለእነዚህ ሀላፊነቶች ክፍሎች አዘጋጁላቸው፣ ይላል ጌታ አምላካችሁ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

፲፳፲ ሀ ቅ.መ.መ. ካስማ።
፲፳፲፪ ሀ ት. እና ቃ. ፲፯፣ ፲፩–፲፪፣ ፲፱–፲፯።
ቅ.መ.መ. ሽማግሌ፣ ቡድን።

፲፳፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. ሰባ።
፲፳፲፩ ሀ ት. እና ቃ. ፭፭፣ ፲፰፣ ፲፯፣ ፲፭።
ለ ቅ.መ.መ. ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች።

፲፳፲፣ ሀ ኤፌ. ፬፣ ፲፩–፲፰።
፲፳፲፰ ሀ ት. እና ቃ. ፳፯፣ ፪።
ቅ.መ.መ. የጋራ ስምምነት።

ክፍል ፤፳፯፤

በመጋቢት ፲፯፤፤፱፩ (እ.አ.አ.)፣ በናቩ ኢለኖይ ውስጥ በአየዋ ክልል ውስጥ ያሉትን ቅዱሳን በሚመለከት ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተሰጠ ራዕይ።

፩–፬፣ ቅዱሳን ከተማዎችን ይስሩ እና የፅዮን ካስማዎችንም ይሰብስቡ።

፩ በአየዋ ክልል ያሉትን ቅዱሳን በሚመለከት የጌታ ፈቃድ ምንድን ነው?

፪ ጌታ እንዲህ ይላል፣ እውነት እላችኋለሁ ᵐበስሜ ራሳቸውን የሚጠሩና ቅዱሳኔ ለመሆን የሚጥሩ፣ የምፈልገውን ቢያደርጉ እና እነርሱን የሚመለከቱ ትእዛዛቴን ቢያከብሩ፣ በአገልጋዬ ጆሴፍ በምመድብላቸው ስፍራዎች ራሳቸውን አብረው ይሰብስቡ፣ እና ለሚመጣው ዘመንም ይዘጋጁ ዘንድ በስሜም ከተማዎችን ይስሩ።

፫ ከናቩ ከተማ የተለየ ከተማ በስሜ ይስሩ፣ እና ስሙም ᵐዛራሔምላ ይሁን።

፬ እና በዚህ ውስጥ ለመኖር ፈቃድ ኖሮ አቸው ከምስራቅ፣ እና ከምዕራብ፣ እና ከሰሜን፣ እና ከደቡብ የመጡት ሁሉ፣ ከዚህ፣ እና ᵐከናሽቪል ከተማ፣ ወይም ከናቩ ከተማ፣ ከመደብኳቸው ᶮካስማዎች ሁሉ ውርሶቻቸውን ያግኙ፣ ይላል ጌታ።

ክፍል ፤፳፯፤

በሐምሌ ፱፣ ፲፯፤፤፱፩ (እ.አ.አ.) በብሪገም ያንግ ቤት ውስጥ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። በዚህ ጊዜ ብሪገም ያንግ የአስራ ሩለቱ ሐዋርያት ቡድን ፕሬዘደንት ነበር።

፩–፫፣ ብሪገም ያንግ ለአገልግሎቱ ተሞግሷል እና ወደፊትም ወደውጪ ከመጓዝ ፋታን አገኝ።

፩ ውድ እና ተወዳጅ ወንድም ᵐብሪገም ያንግ፣ እውነት ጌታ እንዲህ ይልሀል፥ አገልጋዬ ብሪገም፣ እንዳለፉት ጊዜያት ቤተሰብህን እንድትተው አይጠበቅብህም፣ መስዋዕትህ በእኔ ዘንድ ተቀባይነትን አግኝቷልና።

፪ ስለስሜም በጉዞዎችህ ከባድ ስራህን እና ᵐአገልግሎትህን አይቻለሁ።

፫ ስለዚህ ቃሌን ወደውጪ እንድትልክ፣ እና ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እስከ ዘለአለም ᵐቤተሰብህን በልዩ ሁኔታ እንድትንከባከባቸው አዝሀለሁ። አሜን።

ክፍል ፤፳፯፤

ከነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ ለናቩ ኢለኖይ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን ስለሙታን መጠመቅ መመሪያን የያዘ፣ በመስከረም ፭፣ ፲፯፤፤፱፪ (እ.አ.አ.) በናቩ የተጻፈ ደብዳቤ።

፤፳፯፤ ፪ *ሀ* ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—የክርስቶስን ስም በራሳችን ላይ መውሰድ።

ለ ቅ.መ.መ. ካስማ።

ሐ ቅ.መ.መ. ዛራሔምላ።

መ ይህም ናሽቪል፣ ሊ አውራጃ፣ አየዋ ማለት ነው።

ሠ ቅ.መ.መ. ስራዎች።

ረ ቅ.መ.መ. ቤተሰብ።

ሰ ቅ.መ.መ. ያንግ፣ ብሪገም።

ቀ ቅ.መ.መ. ስራዎች።

በ ቅ.መ.መ. ቤተሰብ።

*፩–፬፣ ጆሴፍ ስሚዝ በስደት እና በመከራ
መካከል ይደሰታል፤ ፭–፲፪፣ ስለሙታን
ጥምቀቶችን በሚመለከት መዛግብት መጠ
በቅ አለባቸው።*

፩ ጌታ ለእኔ በገለጠልኝ መጠን ጠላቶቼ
በሚዙሪ እና በዚህ ስቴት ውስጥ ዳግም
እየፈለጉኝ ናቸው፤ እና [ሀ]ያለምክንያትም
እየፈለጉኝ እስከሆነ ድረስ፣ እና በእኔ ላይ
በሚያመጡት ክስ በጎናቸው ጥቂት የሆነ
የፍትህ ወይም የትክክለኛነት ጥላ ወይም
ቀለም የላቸውም፤ እና ጥያቄዎቻቸው
በጨለመ ሀሰት ላይ የተመሰረቱ እስከሆኑ
ድረስ፣ ለራሴ ደህንነት እና ለዚህ ህዝብም
ደህንነት ለአጭር ዘመን ይህን ስፍራ ትቼ
መሄዴ አስፈላጊ እና ጥበባዊ እንደሆነም
አስቤአለሁ። ጉዳዮቻችን በአንድነት ስላ
ሉት ሁሉ ይህን እላለሁ፣ ጉዳዮችን ሁሉ
በፍጥነት እና በትክክለኛው አኳኋን በሚ
ያከናውኑ እና ንብረቶችን በመሸጥ ወይም
ጉዳዩ አስፈላጊ በሚሆንበት ወይም ጉዳዩ
እንደሚፈቅደው በጊዜውም እዳዎቼን ሁሉ
እንዲሰረዙ ለሚያደርጉ ወኪሎች እና ጸሀ
ፊዎች ጉዳዮቼን ትቼአቸዋለሁ። ማእበሉ
እንዳለፈ ባወቅሁ ጊዜ፣ ከዚያም ወደ እና
ንተ ዳግሞ እመለሳለሁ።

፪ እንዳልፍባቸው ስለተጠራሁባቸው
[ሀ]አደገኛ ነገሮችም፣ ለእኔ እንደ ጥቂት ነገር
ነው የሚመስሉኝ፣ የሰው [ለ]ቅናት እና ቁጣ
በህይወቴ ቀናት ሁሉ የየጊዜው እድሌ ነበ
ርና፤ እና እናንተም ልትጠሩት በምትመ
ርጡት ከምድር መመስረት በፊት ለመ
ልካም ወይም ለመጥፎ አላማ [ሐ]የተሾም
ኩኝ ካልሆነ በስተቀር፣ ይህ በምን እንደ
ሚከሰት ሚስጥር ይመስላል። ለራሳችሁም
ፍረዱ። መልካምም ይሁን መጥፎ፣ እግዚ
አብሔር እነዚህን ነገሮች ሁሉ ያውቃል።
ይህም ቢሆን ግን፣ ለመዋኘት የምፈልግ
በት ጥልቅ ውሀ ነው። ለእኔ ሁለተኛ ህይወት
ሆኖልኛል፤ እና እንደ ጳውሎስ [መ]በመከራ
ዎች እደሰታለሁ፤ እስከዚህም ቀን ድረስ
የአባቶቼ አምላክ ከሁሉም አድኖኛልና፣
እና ከዚህም በኋላ ያድነኛልና፤ እነሆ እናም
አስተውሉ፣ ጠላቶቼን ሁሉ አሸንፋለሁ፣
ጌታ አምላክ ተናግሮታልና።

፫ ቅዱሳን ሁሉ ይደሰቱ፣ እና ከመጠ
ንም በላይም ይደሰቱ፤ የእስራኤል [ሀ]አም
ላክ አምላካቸው ነውና፣ እና በሚጨቁኗ
ቸው ራሶች ላይ ሁሉ የጽድቅን ብድራት
መዝኖ ይሰጣቸዋል።

፬ ደግሞም፣ በእውነት ጌታ እንዲህ
ይላል፥ [ሀ]የቤተመቅደሴ ስራ፣ እና የመደብ
ኩላችሁ ስራ ሁሉ ይቀጥሉ እና አያቁሙ፤
እና [ለ]ትጋታችሁ እና የፅናት ስራዎቻችሁ፣
እና ትእግስታችሁ፣ እና ስራዎቻችሁ ይጠ
ንክሩ፣ እና ዋጋችሁን አታጡም ይላል የሰ
ራዊት ጌታ። እና [ሐ]ከጨቆኗችሁም፣ ከእ
ናንተ በፊት የነበሩትን ነቢያትን እና ጻድቅ
ሰዎችን ጨቁነው ነበር። ለዚህም ሁሉ በሰ
ማይ ደመወዝ አለና።

፭ ደግሞም፣ [ሀ]ስለሙታናችሁ [ለ]ጥምቀት
በሚመለከት መልእክትን እሰጣችኋለሁ።

፮ በእውነት ስለሙታናችሁ በሚመለከት
ጌታ እንዲህ ይላል፥ ማንኛችሁም ለሙ
ታናችሁ [ሀ]ስትጠመቁ፣ [ለ]ዘጋቢ ይኑር፣ እና
እርሱም ለጥምቀቶቻችሁ የአይን ምስክር
ይሁን፤ ስለእውነት ይመሰክር ዘንድ በጆ
ሮዎቹም ይስማ፣ ይላል ጌታ፤

፯ [ሀ]መዛግብቶቻችሁን በሚመለከትም
በሰማይ ውስጥ ይመዘገባሉ፤ በምድር

፻፳፯ ፩ ሀ ኢዮብ ፪፥፫፤ ማቴ. ፭፥፲–፲፪፤ ፩ ጴጥ. ፪፥፳–፳፫።
፪ ሀ መዝ. ፳፫። ቅ.መ.መ. ማሳደድ፣ መሳደድ።
ለ ቅ.መ.መ. ቅናት።
ሐ ቅ.መ.መ. ቀድሞ መመረጥ።
መ ፪ ቆሮ. ፯፥፬–፭። ቅ.መ.መ. ጭንቀት።
፫ ሀ ፫ ኔፊ ፲፩፥፲፪–፲፬።
፬ ሀ ት. እና ቃ. ፻፳፬፥፶፭።
ለ ቅ.መ.መ. ትጋት።
ሐ ቅ.መ.መ. ማሳደድ፣ መሳደድ።
፭ ሀ ቅ.መ.መ. ለሙታን ደህንነት።
ለ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣ መጥመቅ—ለሙታን መጠመቅ።
፮ ሀ ፩ ቆሮ. ፲፭፥፳፱፤ ት. እና ቃ. ፻፳፰፥፲፫፣ ፲፰።
ለ ት. እና ቃ. ፻፳፰፥፪–፬፣ ፯።
፯ ሀ ቅ.መ.መ. የሕይወት መፅሐፍ።

ᵃየሚታሰረው ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆ
ናል፣ በምድርም የሚፈታው ሁሉ በሰማ
ያት የተፈታ ይሆናል፤
፳ ᵇክህነትን በሚመለከት፣ በምድር ላይ
ብዙ ነገሮችን ᶜዳግም ልመልስ ነውና፣
ይላል የሰራዊት ጌታ።
፳፩ ደግሞም፣ በቅዱስ ቤተመቅደሴ ᵈየመ
ዝገብ ማከማቻ ውስጥ እንዲቀመጡ፣ ከት
ውልድ ወደ ትውልድም በማስታወሻነት
ይቀመጡ ዘንድ መዛግብት በስርዓት ይጠ
በቁ፣ ይላል የሰራዊት ጌታ።
፳፪ ለቅዱሳን ሁሉ እላለሁ፣ በሚቀጥለው
ሰንበት ስለሙታን የመጠመቅን ርዕስ በመ
ስበኪያው ቆሜ እነርሱን ለማነጋገር በጣም
ታላቅ የሆነ ፈቃድ አለኝ። ነገር ግን ይህ
ከእኔ ሀይል ውጪ ሆኖ ሲገኝ፣ ስለዚህ ርዕስ
እና ስለሌሎች ብዙ ነገሮችም፣ የጌታን ቃል
ከጊዜ ወደጊዜ እፅፋለሁ፣ እና በፖስታም
እልክላችኋለሁ።
፳፫ ጊዜ ስለሌለኝ፣ አሁን ለጊዜው ደብ
ዳቤዬን በዚሁ እፈፅማለሁ፤ ጠላት ዝግጁ
ነውና፣ እና አዳኛችን እንዳለውም፣ የዚህ
አለም ᵉገዢ ይመጣል፣ ነገር ግን በእኔ ላይ
አንዳች የለውም።
፳፬ እነሆ፣ ለእግዚአብሔር የምጸልየው
እናንተ ትድኑ ዘንድ ነው። እና እንደ ጌታ
አገልጋይ፣ እንደ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን
የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ነቢይ
እና ᶠባለራዕይ ራሴን አቀርባለሁ።

ጆሴፍ ስሚዝ።

ክፍል ፤፳፯፤

*ከነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ ለየኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲ
ያን ስለሙታን ጥምቀት ተጨማሪ መመሪያን የያዘ፣ በመስከረም ፭፣ ፲፰፲፱ዓ.ም
(እ.አ.አ.) በናቩ የተጻፈ ደብዳቤ።*

*፩–፫፣ የአካባቢ እና አጠቃላይ መዛግብት
ስለሙታን መጠመቅ መከናወን ማረጋገጥ
አለባቸው፤ ፬–፱፣ ዘገባዎቹም የሚያስ
ተሳስሩ ናቸው እና በምድር እናም በሰ
ማይ የተመዘገቡ ናቸው፤ ፲–፲፭፣ የማ
ጥመቂያ ገንዳው የመቃብር ተምሳሌት
ነው፤ ፲፮–፲፯፣ ኤልያስ ከሙታን ጥም
ቀት ጋር ተዛማጅነት ያለውን ሀይልን
ዳግም መለሰ፤ ፲፰–፳፩፣ ያለፉት ዘመ
ናት ቁልፎች፣ ሀይላት፣ እና ስልጣናት
ሁሉ ዳግም ተመልሰዋል፤ ፳፪–፳፭፣ አስ
ደሳች እና የከበረ ምስራች ለህያው እና
ለሙታን ታውጇል።*

፩ ስፍራዬን ትቼ ከመሄዴ በፊት ከጊዜ
ወደጊዜ እንደምፅፍላችሁ እና ብዙ ርዕሶ
ችን በሚመለከት መግለጫዎች እንደምሰ
ጣችሁ እንዳመለከትኳችሁ፣ በጠላቶቼ
እየተሰደድኩኝ እያለሁ፣ ርእሱ በአዕም
ሮዬ ውስጥ ስላለ እና በስሜቴ ላይ በብር
ቱም ስለሚገፋፉኝ፣ ስለሙታን ᵍመጠመቅ
ርዕስ እቀጥላለሁ።
፪ ዘጋቢውን በሚመለከት ጥቂት የራዕይ
ቃላትን ፅፌላችኋለሁ። ይህን ርዕስ በሚመ
ለከት አሁን የማረጋግጣቸው ጥቂት ተጨ
ማሪ አስተያየቶች አሉኝ። ያም፣ ከዚህ
በፊት በደብዳቤዬ እንደገለፅኩት፣ የአይን
ምስክር የሚሆን፣ እና በጆሮዎቼ ሰምቶ

፲፩ ለ ቅ.መ.መ. ማተም፣ ማስተሳሰር።
፳ ሀ ቅ.መ.መ. የመልክ ጼዴቅ ክህነት።
ለ ቅ.መ.መ. የወንጌል ዳግም መመለስ።
፳፩ ሀ ት. እና ቃ. ፤፳፯፤፡ ፳፱።
፲፩ ሀ ዮሐ. ፲፬፡ ፴፣ ጆ.ስ.ት. ዮሐ. ፲፬፡ ፴ (ተጨማሪ)። ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
፲፪ ሀ ት. እና ቃ. ፤፳፯፡ ፤፳፯፤።
ቅ.መ.መ. ባለራዕይ።
ᶠ፤፳፯፤ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣ መጥመቅ—ለሙታን መጠመቅ።

በጌታ ፊት እውነትን ይመዝገብ ዘንድ ᵐዘጋቢ ማስፈለጉን ነው።

፫ አሁን፣ ከዚህ ጉዳይ ጋር በሚገናኝም፣ ለአንድ ዘጋቢ በሁሉም ጊዜያት ለመገኘት እና ሁሉንም ስራዎች ያከናውን ዘንድ አዳጋች መሆኑን ነው ይህን ችግር ለማስወገድ፣ በእያንዳንዱ ከተማው ዎርዶች የስብሰባ መዛግብትን ያለስህተት ለመጻፍ ብቁ የሆነ ዘጋቢ ለመመደብ ይቻላል፤ እና ቃል ጉባኤውን ለመጻፍም፣ በአይኑ እንዳያቸውና በጆሮዎቹ እንደሰማቸው፣ ቀናትን፣ ስሞችን፣ እና ሌሎችን፣ እና የጉዳይን ሁሉ ታሪኮችን በመመዝገብ፣ መዝገቡን በማረጋገጥ በጣም ጥንቁቅ እና ትክክለኛ ይሁን፤ እሰጣችኋለው፤ በሁለት ወይም በሶስት አንደበት ᵐምስክርነት ሁሉም ቃል ይጸና ዘንድ በዚያ ከነበሩም፣ በሚጠሩበት በማንኛውም ጊዜ ይህን ለማረጋገጥ የሚችሉ የነበሩትን ሶስት ግለሰቦችን ስም ይጻፍም።

፬ ከዚያም፣ ዘገባው እውነት እንደሆነ የሚያስረዳ የፈረመባቸውን የምስክር ወረቀቶች የሚቀበል አጠቃላይ ዘጋቢም ይኑር። ከዚያም የ ቤተክርስቲያኗ አጠቃላይ ዘጋቢ በአጠቃላይ በ ቤተክርስቲያኗ መፅሀፍ ውስጥ ከምስክር ወረቀቶች እና ከነበሩት ምስክሮች ጋር በቤተክርስቲያኗ የተመደቡትን ሰዎች አጠቃላይ ጸባይ እውቀቱን በመጠቀም የተጻፈውን መዝገብ እውነትኛነት እና መዛግብቱም እውነት እንደሆኑ እንደሚያምንም ሊፅፉቸው ይችላል። እና ይህም በአጠቃላይ ቤተክርስቲያኗ መፅሀፍ ውስጥ ሲደረግ፣ መዝገቡም ቅዱስ ይሆናል፣ እና ስነስርዓቱም ልክ በአይኖቹ እንዳያቸው፣ በጆሮዎቹ እንደሰማቸው፣ እና በአጠቃላይ በቤተክርስቲያኗ መፅሀፍ ውስጥም እንደመዘገባቸው ይሆናል።

፭ የእነዚህን ነገሮች ስርዓት በጣም የተለየ ነው በማለት ታስቡ ይሆናል፤ ነገር ግን ይህም የወንጌሉ ᵐእውቀት ሳይኖራቸው ለሞቱት ለሙታን ᵃደህንነት ጌታ ከአለም መመስረት በፊት የሾመውን እና ያዘጋጀውን ስርዓት እና ዝግጅትን በመከተል የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማሟላት ብቻ እንደሆነ ልንገራችሁ።

፮ በተጨማሪም፣ በራዕይ ፳፡፲፪ ውስጥ ተመዝግቦ እንደምታገኙት፣ ባለራዕዩ ዮሐንስ ስለሙታን ርዕስ ሲያሰላስል እንዲህ ነበር ያወጀው—*ሙታንንም ታናናሾችንና ታላላቆቹን በእግዚአብሔር ፊት ቆመው አየሁ፥ መጻሕፍትም ተከፈቱ፤ ሌላ መጽሐፍም ተከፈተ እርሱም የሕይወት መጽሐፍ ነው፤ ሙታንም በመጻሕፍት ተጽፎ እንደ ነበረ እንደ ሥራቸው መጠን ተከፈሉ።*

፯ በዚህ ጥቅስ ውስጥም መፅሀፍት ተከፍተው እንደነበርም ታገኛላችሁ፤ እና ሌላ መጽሐፍም ተከፈተ እርሱም ᵐየሕይወት መጽሐፍ ነው፤ ሙታንም በመጻሕፍት ተጽፎ እንደ ነበረ እንደ ሥራቸው መጠን ተፈረደባቸው፤ በዚህም ምክንያት፣ የተነገረላቸውም መፅሀፍት ስራዎቻቸውን ዘገባ የያዙ መሆን አለባቸው፣ እና በምድር ላይ ተጠብቀው ያሉትን ᵃመዛግብት የሚጠቅስ ነው። እና የህይወት መፅሀፍ የሆነው መፅሀፍም በሰማይ ውስጥ የተጻፈው መዝገብ ነው፤ ይህም መሰረታዊ መርህ ስፍራዬን ትቼ ከመሄዴ በፊት በላኩላችሁ ደብዳቤ ውስጥ የነበረው ትእዛዝ ከሰጣችሁ ራዕይ ጋር በግልፅም ይስማማል—መዛግብቶቻችሁ ሁሉ በሰማይ የተመዘገቡ ናቸው።

፰ አሁን፣ ለዚህ ስነስርዓት መሰረት የሚሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ራዕይ አማካይነት የሚገኘው የክህነት ᵐሀይል ነው፣ በዚህም በምድር ᵃየምታስሩት ሁሉ በሰማያት የታሰረ ይሆናል፣ እና በምድርም የፈታችሁ ሁሉ በሰማያት የተፈታ ይሆናል። ወይም፣

፪ ሀ ት. እና ቃ. ፲፳፯፡፯።
፫ ሀ ቅ.መ.መ. ምስክር።
፭ ሀ ፩ ጴጥ. ፬፡፮።
ለ ቅ.መ.መ. ለሙታን ደህንነት።
፯ ሀ ራዕ. ፳፡፲፪፤ ት. እና ቃ. ፲፳፯፡፯–፯። ቅ.መ.መ. የሕይወት መፅሐፍ።
ለ ት. እና ቃ. ፳፭፡፩።
፰ ሀ ቅ.መ.መ. ሀይል፤ ክህነት።
ለ ቅ.መ.መ. ማተም፣ ማስተሳሰር።

በሌላ ቃላት፣ የትርጉሙን ሌላ አስተያየት በመውሰድ፣ በምድር የመዘገባችሁት ሁሉ በሰማይ የተመዘገበ ይሆናል፣ እና በምድርም የማትመዘግቡትም ሁሉ በሰማያት አይመዘገብም፤ ሐለደህንነታቸው እግዚአብሔር አለም ከመፈጠሩ በፊት ባዘጋጀው መስርዓት መሰረት፣ ስለሙታናቸው በተጠበቁት መዛግብቶቻቸው መሰረት እነዚህን ስነስርዓቶች ለራሳቸው ወይም በወኪላቸው ቢያከናውኑትም፣ ከመጻህፍቱ መሰረት፣ ሙታናችሁ እንደ ስራቸው ይፈረድባቸዋል።

፱ የተነጋገርንበት—በምድር የሚመዘገበው ወይም የሚያስረው እና በሰማይ የሚያስረው ሀይል ለአንዳንዱ በጣም ደፋር የሆነ ትምህርት ይመስላል። ይሁን እንጂ፣ በአለም ዘመናት ሁሉ፣ ጌታ ለማንም ሰው፣ ወይም ለተለያዩ ሰዎች፣ በእውነት ራዕይ የክህነት መዘመንን በሚሰጥበት በማንኛውም ጊዜ ይህ ሀይል ዘወትር ይሰጣል። ከዚህ በኋላ፣ ለበስልጣን፣ በጌታ ስም፣ እነዚህ ሰዎች ምንም ቢያደርጉ፣ እና በእውነት እና በታማኝነት ቢያደርጉት፣ እና የእነዚህን ትክክለኛ እና የታመኑ መዛግብትን ቢጠብቁ፣ በምድር ላይ እና በሰማያት ውስጥ ህግ ይሆናል፣ እና በታላቁ ሐያህዌህ ህግጋት መሰረት ሊሰረዝም አይችልም። ይህም የታመነ አባባል ነው። ማን ይሰማዋል?

፲ ደግሞም፣ አስቀድሞ ስለተፈጸመው፣ ማቴዎስ ፲፮፡፲፰፣ ፲፱፡ እኔም እልሀለሁ፣ አንተ ጴጥሮስ ነህ፥ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፣ የሲዖል ደጆችም አያሸንፏትም። የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሀለሁ፤ በምድር የምታስረው ሁሉ በሰማያት የታሰረ ይሆናል፣ በምድርም የምትፈታው ሁሉ በሰማያት የተፈታ ይሆናል።

፲፩ አሁን የዚህ ጉዳይ ታላቅ እና የከበረው ሚስጥር፣ እና በፊታችን የተዘረጋው እጅግ የላቀው መልካም ነገር የቅዱስ ክህነት ሀይላትን በማግኘት ላይ የተመሰረተ ነው። እነዚህ ሀቁልፎች ለተሰጡትም ለእርሱ ስለሰው ልጆች፣ ስለሙታን እና ህያዋን ለደህንነት በሚመለከት ተጨባጭ እውቀትን ለማግኘት ችግር አይኖርም።

፲፪ በዚህም ውስጥ ሀግርማ እና ለክብር፣ ሐህያውነት እና ዘለአለማዊ ህይወት አለ—የውሀ ጥምቀት ስነስርዓት፣ በዚህም በሞት ምሳሌነት መመጥለቅ፣ አንዱ መሰረታዊ መርህ ከሌላው ጋር እንዲስማማ፤ በውሀ ውስጥ መጠለቅና ከውሀው መውጣት እንደ ሟች ከመቃብር በትንሳኤ በሚነሱበት ምሳሌ ነው፤ ከዚህ በኋላም፣ ይህ ስነስርዓት የተመሰረተውም እንደ ሞት አምሳል የሆነው የሙታን ጥምቀት ስነስርዓትን ግንኙነት ለመስራት ነው።

፲፫ በዚህም ምክንያት፣ ሀየማጥመቂያ ገንዳው የተመሰረተው በመቃብር ለአምሳል ሲሆን በዝቅተኛ ስፍራም የሚቀመጥ ሆኖ፣ እና አንዱም ከሌላው ጋር ይወያይ ዘንድ ለህያዋንም ሆነ ለሙታን ሁሉም ነገር አምሳያ እንዳለው ለማሳየት ህያዋን እንዲ ሰበሰቡ የታዘዙበት ስፍራ ነው—ጳውሎስ እንዳወጀውም፣ ምድራዊው ከሰማያዊ ጋር ይስማማ ዘንድ ነው፣ ፩ ቆሮንቶስ ፲፭፡፴፮፣ ፴፯፣ እና ፴፰፡

፲፬ ነገር ግን አስቀድሞ ፍጥረታዊው ቀጥሎም መንፈሳዊው ነው እንጂ መንፈሳዊው መጀመሪያ አይደለም። የፊተኛው ሰው ከምድር ምድራዊ ነው፤ ሁለተኛው ሰው ከሰማይ የመጣ ጌታ ነው። ምድራዊው እንደ ሆነ ምድራዊ የሆኑት ደግሞ እንዲሁ ናቸው፥ ሰማያዊው እንደ ሆነ ሰማያዊ የሆኑት ደግሞ እንዲሁ ናቸው። በእው

፳ ሐ ቅ.መ.መ. ለሙታን ደህንነት።
መ ቅ.መ.መ. ስነስርዓቶች።
፱ ሀ ቅ.መ.መ. ዘመን።
ለ ቅ.መ.መ. ስልጣን።
ሐ ቅ.መ.መ. ያህዌህ።

፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
ለ ቅ.መ.መ. ደህንነት።
፲፪ ሀ ቅ.መ.መ. ክብር።
ለ ቅ.መ.መ. ክብር።
ሐ ቅ.መ.መ. የማይሞት፣ አለሟችነት።

መ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣ መጥመቅ—በማጥለቅ መጥመቅ።
፲፫ ሀ ት. እና ቃ. ፪፳፩፡፳፱።
ለ ቅ.መ.መ. ምሳሌዎች።

ነትም የተመዘገቡት፣ የዚያንም ሙታና ችሁን በሚመለከትም ምድራዊ መዛግብት እንዳሉ ሁሉ፣ የሰማያዊ መዛግብትም ይኖ ራሉ። ስለዚህ ይህም ᵐየሚያትም እና የሚ ያስተሳስር ሀይል ነው፣ እና ቃሉም በአንድ ትርጉም፣ ᵃበእውቀት ᵐቁልፍ ላይ የተመሰ ረቱ የመንግስት ቁልፎች ናቸው።

፲፭ አሁንም፣ ውድ ወንድሞቼ እና እህቶቼ፣ ᵐደህንነታችንን በሚመለከትም፣ እነዚህ ሙታንንና ህያዋንን የሚመለከቱ መሰረታዊ መርሆች በቀላል እንደማይታ ለፉ ላረጋግጥላችሁ። ደህንነታቸውም ለእኛ ደህንነት አስፈላጊ እና መሰረታዊ ነው፣ ጳውሎስ ስለአባቶች እንዳለው—ያለ እኛ ፍጹማን ሊሆኑ አይችሉም—ወይም እኛ ያለሙታኖቻችን ᵃፍጹም ልንሆን አንች ልም።

፲፮ አሁንም፣ የሙታን ጥምቀት በሚ መለከት፣ ሌላ የጳውሎስን ጥቅስ እሰጣች ኋለሁ፣ ፩ ቆሮንቶስ ፲፭፡፡፳፱፡ *እንዲያማ ካልሆነ፣ ስለ ሙታን የሚጠመቁ ምን ያደ ርጋሉ? ሙታንስ ከቶ የማይነሡ ከሆነ፣ ስለ እነርሱ የሚጠመቁ ስለ ምንድር ነው?*

፲፯ ደግሞም፣ ከዚህ ጥቅስ ጋር በተገናኘ አይኑን በክህነት ስልጣን ᵐዳግም መመለስ ላይ፣ በመጨረሻዎቹ ቀናት ላይ ለሚገለ ጡት ክብሮች፣ እና ከሁሉም ርእሶች በላይ የከበረው ይህ፣ እንዲሁም ለሙታን መጠ መቅ በዘለአለም ወንጌል ክፍል ስለሆነው ትኩረትን ሰጥቶት ከነበረው ከነብያቱ የአ ንዱን ጥቅስ እሰጣችኋለሁ፤ በመጨረሻው ምዕራፍ፣ አንቀፅ ፭ እና ፮ ውስጥ ሚልክ ያስ እንዳለው፥ *እነሆ፣ ታላቁና የሚያስ ፈራው የእግዚአብሔር ቀን ሳይመጣ ነቢ ዩን ᵃኤልያስን እልክላችኋለሁ። መጥቼም ምድርን በእርግማን እንዳልመታ እርሱ የአ ባቶችን ልብ ወደ ልጆች፣ የልጆችንም ልብ ወደ አባቶች ይመልሳል።*

፲፰ ለዚህም ᵐግልጽ የሆነ ትርጉም ለመ ስጠት በቻልኩ ነበር፣ ነገር ግን እንዳለም አላማዬን ያሟላ ዘንድ ይህ በቂ ነው። በዚህ ጉዳይ፣ በአባቶች እና ልጆች መካከል በአ ንድ በተወሰነ ርዕስ ወይም በሌላ፤ አንድ ወይም ሌላ የሚያስተሳስር ᵃግንኙነት ከሌለ ምድር በእርግማን እንደምትመታ ማወቁ በቂ ነው—እና እነሆ ያ ርዕስ ምንድን ነው? ይህም ለሙታን ᵐመጠመቅ ነው። ያለእ ነርሱ ፍጹም ልንሆን አንችልም፤ ወይም እነርሱም ያለእኛ ፍጹማን ሊሆኑ አይች ሉም። እነርሱም ይሁን እኛ በወንጌሉ ካል ሞቱት በስተቀር ፍጹም ልንሆን አንች ልም፤ አሁን መግባት በጀመረው ᵐየዘመን ፍጻሜ መግቢያ ውስጥ ሙላት እና የተፈ ጸመ እና ፍጹም አንድነት፣ እና ከአዳም ቀናት እስከ አሁን የተገለጡት የዘመናት፣ ቁልፎች፣ እና ሀይላት፣ እና ክብሮች መተ ሳሰራቸው አስፈላጊ ነውና። እና ይህም ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን ከዚህ ምድር ᵐመመ ስረት ጀምሮ ያልተገለጡት፣ ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ተሰውረው የነበሩት፣ እነዚያ ነገሮች ᶜለህጻናት እና ለሚጠቡት በዚህ በዘ መን ፍጻሜ ይገለጣሉ።

፲፱ አሁን፣ በተቀበልነው ወንጌል ውስጥ ምን እንሰማለን? የደስታ ድምፅ! የምህረት ድምፅ ከሰማይ፤ እና ከምድር ውስጥም ᵐየእውነትን ድምፅ፤ የምስራች ዜና ለሙ ታን፤ ከህያውና ከሙታን የደስታ ድምፅ፤ የታላቅ ደስታን ᵃየምስራች ነው። የምስ ራች የሚናገር፣ ሠላምን የሚያወራ፣ የመ ልካምን ወሬ የምስራች የሚናገር፣ ስለመ

፲፩ ᵐ ቅ.መ.መ. ማተም፣ ማስተሳስር።
ᵃ ጆ.ስ.ት. ሉቃ. ፲፩፡፡፶፫ (ተጨማሪ)።
ᵐ ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።

፲፩ ᵐ ቅ.መ.መ. ለሙታን ደህንነት።
ᵃ ዕብ. ፲፩፡፡፴፯ ቅ.መ.መ. ፍጹም።

፲፯ ᵐ ቅ.መ.መ. የወንጌል ዳግም መመለስ።
ᵃ ᵐ ኔፊ ፳፩፡፡፭–፮፣ ት. እና ቃ. ፪፡፡ ᵐ፲፣ ᵐ፲ᵐ–ᵐ፲፯። ቅ.መ.መ. ኤልያስ።

፲ᵐ ᵐ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፡ᵐ፲፯–ᵐ፲ᵐ።
ᵃ ቅ.መ.መ. ስነስርዓቶች—የወኪል ስነስርዓት፣ የትውልድ ሐረግ።
ᶜ ት. እና ቃ. ᵐ፳ᵐ፡፡ᵐ፳ᵐ–ᵐ፣ ᵐᵐᵐ፯፡፡፮–፯።
ᵐ ቅ.መ.መ. ዘመን።
ᵐ ት. እና ቃ. ᵐ፲ᵐ፡፡ᵐ፲ᵐ።
ᶜ ማቴ. ᵐ፲ᵐ፡፡ᵐ፳ᵐ፣ ሉቃ. ᵐ፣ ᵐ፳ᵐ፣ አልማ ᵐᵐᵐ፡፡ᵐ፳ᵐ።

፲ᵐ ᵐ መዝ. ᵐᵐᵐ፡፡ᵐ፣ ᵐ–ᵐᵐᵐ።
ᵃ ሉቃ. ᵐ፡፡ᵐ።

ዳን የሚያወራ፣ ፅዮንንም አምላክሽ ነግሶ አል! የሚል ሰው [ሐ]እግሮቹ በተራሮች ላይ እጅግ እንዴት ያማሩ ናቸው። እንደ ቀር ሜሎስ [መ]ጠል፣ እንደዚህም የእግዚአብሔር እውቀት በእነርሱ ላይ ያርፋል!

፳ ደግሞም፣ ምን እንሰማለን? [ሀ]ከከሞራ የደስታ ዜና! የሰማይ መልአክ [ለ]ሞሮኒ የነ ቢያትን ፍጻሜ—የሚገለጠውን [ሐ]መፅ ሀፍ ሲያውጅ። የጌታም ድምፅ [መ]በፈየት፣ በሰነካ የግዛት ክፍል ዱር ውስጥ ሶስቱ ምስ ክሮች ስለመፅሐፉ [ሠ]እንዲመሰክሩ ሲያ ውጅ! [ረ]የሚካኤል ድምፅም በሰስኳሀና ወንዝ ዳር ዲያብሎስን እንደ [ሰ]ብርሀን መል አክ ሲቀርብ በማየት ሲመረምር! [ሸ]የጴጥ ሮስ፣ የያዕቆብ፣ እና የዮሐንስ ድምፅ በበረሀ ውስጥ በሀርመኒ፣ ሰስኳሀና የግዛት ክፍል ውስጥ እና በኮልስቪል፣ ብሩም የግዛት ክፍል ውስጥ በሰስኳሀና ወንዝ ላይ ራሳቸ ውን እንደ መንግስት እና እንደ ዘመን ፍጻሜ [ቀ]ቁልፎች ያዥ በመግለፅ ሲያውጁ!

፳፩ ደግሞም፣ በአረጋዊው [ሀ]አባት ዊት መር ቤት ውስጥ በፈየት፣ ሰነካ የግዛት ክፍል ውስጥ እና በተለያዩ ጊዜያት፣ እና በተለያዩ ስፍራዎች በየኋለኛው ቀን ቅዱ ሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ጉዞ ዎች እና ፈተናዎች ሁሉ የእግዚአብሔርን ድምፅ! እና ሚካኤል የመላእክት አለቃ ድምፅ፤ [ለ]የገብርኤል፣ [ሐ]የሩፋኤል፣ እና የተለያዩ [መ]መላዕክት፣ ከሚካኤል ወይም [ሠ]ከአዳም እስከ አሁን [ረ]ዘመን ድረስ፣ በት ዕዛዝ ላይ ትዕዛዝ፣ [ሰ]በስርዐት ላይ ስርዐ ትን፣ ጥቂት በዚህ፣ ጥቂት በዚያ በመስ ጠት፤ ወደፊት የሚመጣውን በማወጅ፣ [ሸ]ተስፋችንን በማረጋገጥ፣ ማፅናኛ በመስ ጠት፣ ሁሉም ዘመኖቻቸውን፣ መብቶቻ ቸውን፣ ቁልፎቻቸውን፣ ክብሮቻቸውን፣ ምስጋናዎቻቸውን፣ እና ክብሮቻቸውን፣ እና የክህነት ሀይሎቻቸውን ሲያውጁ ነው!

፳፪ ወንድሞች፣ ለዚህ ታላቅ ስራ ወደ ፊት አንሄድምን? ወደኋላ ሳይሆን ወደፊት ሂዱ። በርቱ፣ ወንድሞች፤ እና ወደ ድል ሂዱ! ልባችሁ ይደሰቱ፣ እና በጣምም ተደ ሰቱ። ምድርም በድንገት [ሀ]ትዘምር። ሙታ ንም ከአለም ፍጥረት በፊት ለተመደበው፣ [ለ]ከወህኒም [ሐ]እንድናድናቸው ስላስቻለን ለንጉስ [መ]አማኑኤል የዘለአለማዊ ምስጋና መዝሙርን ይናገሩ፤ እስረኞቹ በነጻ ይሄዳ ሉና።

፳፫ [ሀ]ተራሮችም በደስታ ይጮሁ፣ እና ሸለቆዎች ሁሉ በጎላ ድምፅ አልቅሱ፤ እና እናንት ባህሮች እና ደረቅ ምድራት ሁሉ የዘለአለም ንጉሳችሁን አስደናቂነት ተና ገሩ! እና እናንት ወንዞች፣ እና ጅረቶች፣ እና ትንንሽ ወንዞችም በደስታም ፍሰሱ። የሜዳው ጫካዎች እና ዛፎች ሁሉ ጌታን ያመስግኑ! እና እናንት ጠንካራ [ለ]አለቶችም በደስታ አልቅሱ። እና ጸሀይ፣ ጨረቅ፣ እና [ሐ]የአጥቢያ ኮከቦችም በአንድነት ዘምሩ፣ እና የእግዚአብሔር ልጆች ሁሉ በደስታ እልል በሉ። እና ዘለአለማዊ ፍጥረቶችም ስሙን ለዘለአለም ያውጁ። ደግሞም እላ ለሁ፣ በጆሮዎቻችን ስለክብር፣ እና ደህን

፲፱ ሐ ኢሳ. ፶፪፥፯–፲፤
ሞዛያ ፲፭፥፲፫–፲፰፤
፫ ኔፊ ፳፥፵።
መ ዘዳግ. ፴፪፥፪፤
ት. እና ቃ. ፻፳፩፥፵፭።
፳ ሀ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፶፩–፶፪።
ቅ.መ.መ. የከሞራ ኮረብታ።
ለ ቅ.መ.መ. ሞሮኒ፣
የሞርሞን ልጅ።
ሐ ኢሳ. ፳፱፥፬፣ ፲፩–፲፬፤
፪ ኔፊ ፳፯፥፯–፳፱።
ቅ.መ.መ. መፅሐፈ ሞርሞን።
መ ቅ.መ.መ. ፈየት፣ ኒው
ዮርክ (ዮ.ኤስ.ኤ.)።
ሠ ት. እና ቃ. ፲፯፥፩–፫።
ረ ት. እና ቃ. ፳፯፥፲፩።
ቅ.መ.መ. አዳም።
ሰ ፪ ቆሮ. ፲፩፥፲፬።
ሸ ት. እና ቃ. ፳፯፥፲፪።
ቀ ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
፳፩ ሀ ይህም ፒተር ዊትመር
ቀዳማዊ ማለት ነው።
ለ ቅ.መ.መ. ገብርኤል።
ሐ ቅ.መ.መ. ራፋኤል።
መ ቅ.መ.መ. መላእክት።
ሠ ት. እና ቃ. ፻፯፥፶፫–፶፮።
ረ ቅ.መ.መ. ዘመን።
ሰ ኢሳ. ፳፰፥፲።
ሸ ቅ.መ.መ. ተስፋ።
፳፪ ሀ ኢሳ. ፵፱፥፲፫።
ለ ኢሳ. ፳፬፥፳፪፤
ት. እና ቃ. ፸፯፥፸፪–፸፬።
ሐ ቅ.መ.መ. ቤዛ፣
ማዳን፣ ቤዛነት።
መ ኢሳ. ፯፥፲፬፤
አልማ ፭፥፶።
ቅ.መ.መ. አማኑኤል።
፳፫ ሀ ኢሳ. ፵፬፥፳፫።
ለ ሉቃ. ፲፱፥፵።
ሐ ኢዮብ ፴፰፥፯።

ነት፣ እና [መ]ህያውነት፣ እና [ሠ]ስለዘለአለማዊ ህይወት፤ ስለመንግስታት፤ አለቅነትና ስልጣናት የሚያውጀው ከሰማያት የምንሰማው ድምጽ እንዴት የከበረ ነው!

፳፬ እነሆ፣ የጌታ ታላቅ [ሀ]ቀን ቀርቧል፤ እና ነገር ግን እርሱ እንደ አንጥረኛ እሳትና እንደ አጣቢ ሳሙና ነውና የሚመጣበትን ቀን [ለ]መታገሥ የሚችል ማን ነው? እርሱስ በተገለጠ ጊዜ የሚቆም ማን ነው? ለእግዚአብሔር በጽድቅ ቍርባንን ያቀርቡ ዘንድ፣ እርሱም ብርን [ሐ]እንደሚያነጥርና እንደሚያጠራ ሰው ይቀመጣል፥ [መ]የሌዊንም ልጆች ያጠራል፥ እንደ ወርቅና እንደ ብርም [ሠ]ያነጥራቸዋል። ስለዚህ፣ እንደ ቤተክርስቲያንና እንደ ህዝብ እና እንደ የኋለኛውም ቀን ቅዱሳን የፅድቅ ለጌታ [ረ]መጽዋዕትን እናቅርብ፤ እና በመጨረሻም በቅዱስ ቤተመቅደሱ ውስጥ፣ ለተቀባይነት ሁሉ ብቁ የሆነውን የሙታናችንን [ሰ]መዛግብት የያዘውን መፅሀፍ እናቅርብ።

፳፭ ወንድሞች፣ በዚህ ርዕስ ላይ የምላችሁ ብዙ ነገሮች አሉኝ፤ ነገር ግን ለጊዜው አበቃለሁ፣ እና ርዕሱንም በሌላ ጊዜ እቀጥላለሁ። እኔ፣ እንደ ወትሮው ሁሉ፣ ትሁት አገልጋያችሁ እና የማይቀየር ባልንጀራችሁ ነኝ፣

ጆሴፍ ስሚዝ።

ክፍል ፻፳፱

በየካቲት ፱፣ ፲፰፻፵፫ (እ.አ.አ.) የአገልጋይ መላዕክት እና የመናፍስትን ትክክለኛ ተፈጥሮን ለመለየት የሚቻልበትን ሶስት ታላላቅ ቁልፎች ለማሳወቅ ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የሰጣቸው መመሪያዎች።

፩–፫፣ ከሞት የተነሱ እና የመንፈስ አካላት በሰማያት ውስጥ አሉ፤ ፬–፱፣ ከመጋረጃው አልፈው የሚመጡ መልእክተኞችን ለይቶ የማወቂያ ቁልፎች ተሰጥተዋል።

፩ ሁለት አይነት [ሀ]የሰማይ ፍጥረታት አሉ፣ እነርሱም፥ [ለ]ከሞት የተነሱ ሰዎች፣ የስጋ እና የአጥንት አካል ያሏቸው [ሐ]መላዕክት—

፪ ለምሳሌ፣ ኢየሱስ፥ *በእኔ እንደምታዩት፥ መንፈስ [ሀ]ሥጋና አጥንት የለውምና እኔን ዳስሳችሁ እዩ አላቸው።*

፫ ሁለተኛ፥ ከሞት ያልተነሱ፣ ነገር ግን ያንን አይነት ክብር የሚወረሱ፣ ፍጹም የሆኑ [ሀ]የጻድቅ ሰዎች [ለ]መናፍስት።

፬ ከእግዚአብሔር መልእክት አለኝ ብሎ መልእክተኛ ሲመጣ፣ እጆቻችሁን ስጡት እና ከእናንተም እጆች ጋር እንዲጨባበጥ ጠይቁት።

፭ መልአክ ከሆነ ይህን ያደርጋል፣ እና እጁንም በመዳደስ ይሰማችኋል።

፮ ፍጹም የሆነ የጻድቅ ሰው መንፈስ ከሆነ በክብሩ ይመጣል፤ ሊመጣም የሚችልበት መንገድ ይህ ብቻ ነውና—

፯ ከእጆቻችሁም ጋር እንዲጨባበጥ ጠይቁት፣ ነገር ግን አይንቀሳቀስም፣ ምክንያቱም ይህ ፍጹም የሆነው ሰው ይታለል ዘንድ ከሰማይ ስርዓት ጋር የሚቃረን ነውና፤ ነገር ግን መልዕክቱን ያበስራል።

፳፫ መ ቅ.መ.መ. የማይሞት፣ አለሟችነት።
ሠ ቅ.መ.መ. የዘለዓለም ህይወት።
፳፬ ሀ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
ለ ሚል. ፫፥፩–፫።
ሐ ፫ ኔፊ ፳፬፥፪–፫።
ቅ.መ.መ. ምድር—ምድርን ማፅዳት።
መ ዘዳግ. ፲፥፰፤ ት. እና ቃ. ፲፫፤ ፻፳፬፥፴፱።
ሠ ዘካ. ፲፫፥፱።
ረ ት. እና ቃ. ፹፬፥፴፩።
ቅ.መ.መ. በኩራት።
ሰ ት. እና ቃ. ፻፳፯፥፱።
ቅ.መ.መ. የትውልድ ሐረግ።
፻፳፱ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. ሰማይ።
ለ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
ሐ ቅ.መ.መ. መላእክት።
፪ ሀ ሉቃ. ፳፬፥፴፱።
፫ ሀ ዕብ. ፲፪፥፳፫፤
ት. እና ቃ. ፸፮፥፷፱።
ለ ቅ.መ.መ. መንፈስ።

፳ ᵐዲያብሎስ በብርሀን መልአክ አምሳል ቢሆን፣ እጆቻችሁንም እንዲጨብጥ ብት ጠይቁት እጁንም ይሰጣችኋል፣ እና ምንም ነገር አይሰማችሁም፤ በዚህም ልታውቁት ትችላላችሁ።

፳፩ እነዚህም ከእግዚአብሔር የመጡ አገ ልግሎቶች እንደሆኑ ለማወቅ የምትችሉባ ቸው ሶስት ታላቅ ቁልፎች ናቸው።

ክፍል ፤፴

በሚያዝያ ፪፣ ፲፰፤፤፴፫ (እ.አ.አ.) በራመስ ኢለኖይ ውስጥ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተሰጡ የመመሪያ ነገሮች።

፩–፫፣ አብና ወልድ ለሰዎች በግል ሊገ ለጡ ይችላሉ፤ ፬–፯፣ መላዕክት በሰለስቲ ያል አለም ውስጥ ይኖራሉ፤ ፰–፱፣ ሰለ ስቲያላዊ ምድር ታላቅ ኡሪምና ቱሚም ትሆናለች፤ ፣–፲፩፣ ወደ ሰለስቲያል አለም ለሚገቡት ሁሉ ነጭ ድንጋይ ተሰጥቷል፤ ፲፪–፲፯፣ የዳግም ምፅዓት ጊዜ ከነቢያት ተሰውሯል፤ ፲፰–፲፱፣ በዚህ ህይወት የተ ገኘው የመረዳት ችሎታ በትንሳኤ ጊዜ አብሮን ይነሳል፤ ፳–፳፩፣ ሁሉም በረከ ቶች ህግን በማክበር ይመጣሉ፤ ፳፪–፳፫፣ አብና ወልድ የሰጋ እና አጥንት አካል አላ ቸው።

፩ አዳኛችን በሚገለጥበት ጊዜ እርሱ እንዳለ ᵐእናየዋለን። እርሱም እንደ እኛው ᵃሰው እንደሆነም እናያለን።

፪ እና በዚህ በመካከላችን የሚገኘው ማህ በራዊ ግንኙነት፣ አሁን የማናገኘውን ነገር ግን ᵐዘለአለማዊ ክብር ተጨምሮበት፣ በዚ ያም እናገኘዋለን።

፫ ዮሐንስ ፲፩፡፳፫—በዚያ አንቀፅ ውስጥ ᵐየአብ እና ᵃየወልድ መገለጥ፣ በተናጠል ᵃየታዩበት ነው፤ እና አብ እና ወልድ በሰው ልብ ውስጥ ᵐያድራሉ የሚለው አስተሳሰብ የድሮ የሀይማኖት ቡድኖች ሀሳብ ነው፣ እና ሀሰትም ነው።

፬ የእግዚአብሔር ᵐጊዜ፣ የመላዕክት ጊዜ፣ የነቢያት ጊዜ፣ እና የሰው ጊዜ አቆ ጣጠር እንደየሚኖሩበት ፕላኔት መሰረት አይደለም?—የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ

፭ አዎን ብዬም እመልሳለሁ። ነገር ግን ከዚህ ምድር የሆኑ ወይም የነበሩ ካልሆኑ በስተቀር፣ የሚያገለግሉ ᵐመላዕክት አይ ኖሩም።

፮ መላእክት ይህን ምድር በሚመስል ፕላ ኔት አይኖሩም።

፯ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት፣ በመ ስታወት እና ᵐእሳት ᵃባህር አለም ላይ፣ ሁሉም ነገሮች ጥንት፣ አሁን፣ እና ወደ ፊት ለክብራቸው በሚገለጥበት፣ እና ይህም በጌታ ፊት በሚቀጥልበት ሁኔታ ይኖራሉ።

፰ እግዚአብሔር የሚኖርበት ስፍራ ታላቅ ᵐኡሪምና ቱሚም ነው።

፱ ᵐምድር፣ በተቀደሰበት እና ዘለአለ ማዊ ሁኔታ በጥራት ትሰራለች እና በው

፰ *ሀ* ፪ ቆሮ. ፣፩፡፣፲፩፣ ፪ ኔፊ ፱፡፱።
፤፴ ፩ *ሀ* ፩ ዮሐ. ፫፡፪፣ ሞሮኒ ፯፡፴፰። ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
ለ ሉቃ. ፳፩፡፴፯–፴። ፪ *ሀ* ቅ.መ.መ. የሰለስቲያል ክብር።
፫ *ሀ* ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ—እግዚአብሔር አብ።
ለ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ—እግዚአብሔር ወልድ።
ሐ ት. እና ቃ. ፣፲፫፡፩።
መ ት. እና ቃ. ፤፴፡፳፪። ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ።
፬ *ሀ* ፪ ጴጥ. ፫፡፣፣ አብር. ፫፡፬–፣፣ ደግሞም በአብር. ቅርፅ ፪፣ ስዕል ፩ን ተመልከቱ።
፭ *ሀ* ቅ.መ.መ. መላእክት።
፮ *ሀ* ኢሳ. ፴፫፡፣፲፩።
ለ ራዕ. ፬፡፮፣ ፣፲፭፡፪።
፰ *ሀ* ቅ.መ.መ. ኡሪም እና ቱሚም።
፱ *ሀ* ት. እና ቃ. ፫፯፡፩። ቅ.መ.መ. ምድር—የምድር የመጨረሻ ሁኔታ።

ስጢም ለሚኖሩት እንደ ኡሪምና ቱሚም ትሆናለች፣ በዚህም የዝቅተኛውን መንግስት፣ ወይም የታችኛው ስርዓት መንግስታትን ሁሉ በሚመለከት ነገሮች ሁሉ በእዚያ ለሚኖሩበት ይገለጥላቸዋል፤ እና ይህች ምድርም የክርስቶስ ትሆናለች።

፲ ከዚያም በራዕይ ፪፡፲፯ ውስጥ የተጠቀሰው ነጭ ድንጋይም አንድ ለሚቀበለው ለእያንዳንዱ ሰው የመንግስት ከፍተኛውን ስርዓትን የሚመለከቱ ነገሮችን እንዲያውቁባቸው የሚደረግበት ኡሪምና ቱሚም ይሆናል፤

፲፩ እና ወደ ሰለስቲያል መንግስት ለሚመጡትም ከሚቀበሉት በስተቀር ማንም የማያውቀው አዲስ ᵐስም የሚጻፍበት ᵃነጭ ድንጋይ ለእያንዳንዱ ተሰጥቷል። አዲሱ ስምም እንደቁልፍ የሆነ ቃል ነው።

፲፪ የሰው ልጅ ከመምጣቱ በፊት ብዙ ደም መፋሰስን የሚያስከትሉ ᵐችግሮች የሚጀምሩት ᵃበደቡብ ኬሮላይና እንደሆነ በጌታ አምላክ ስም እተነብያለሁ።

፲፫ ይህም ምናልባት በባሪያ ጥያቄ ይነሳ ይሆናል። በታህሳስ ፳፭፣ ፲፰፻፴፪ (እ.አ.አ.) ስለዚህ ርዕስ በቅንነት እየጸለይኩ ሳለሁ፣ ይህን ድምፅ አወጀልኝ።

፲፬ በአንድ ወቅት የሰውን ልጅ ᵐየምጻት ጊዜ ለማወቅ በቅንነት ስጸልይ ነበር፣ ድምፅም የሚከተለውን ሲደጋግም የሰማሁት፥

፲፭ ልጄ ጆሴፍ፣ ሰማንያ አምስት አመት እስኪሆንህ ብትኖር፣ የሰውን ልጅ ፊት ለማየት ትችላለህ፤ ስለዚህ ይህ ይብቃህ፣ እናም በዚህም ጉዳይ ከዚህ በላይ አታስቸግረኝ።

፲፮ ይህ የተጠቀሰው ምጽአት ስለአንድ ሺህ ዘመን መጀመሪያ ይሁን ወይም ከዚህ በፊት የሆነ መገለጥ ወይም መሞት እንዳ ለብኝ እና በዚህም ፊቱን የማይ እንደሆ ነም ለመወሰን ባለመቻል እንደዚህም ተተቼ ነበር።

፲፯ የሰው ልጅ መምጫ ከዚህ ጊዜ በፊት ቀድሞም እንደማይሆን አምናለሁ።

፲፰ በዚህ ህይወት የምናገኘው ማንኛውም ᵐየመረዳት ችሎታ መሰረታዊ መርህ፣ ይህም ᵃከሞት ስንነሳ አብሮን ይነሳል።

፲፱ እና አንድ ሰው ᵐበትጋቱ እና ᵃበታዛዥነቱ ከሌላው ሰው በላይ ተጨማሪ ᶜእውቀትን እና የመረዳት ችሎታን በዚህ ህይወት ቢያገኝ፣ በሚመጣው አለምም ውስጥ በበለጠ ᵐየተሻለ ሁኔታ ይኖረዋል።

፳ ይህ አለም ከመመስረቱ ᵐአስቀድሞ ሁሉም ᵃበረከቶች የሚመረኮዙበት በሰማያት ውስጥ ሊሻር የማይችል የታወጀ ᶜህግ አለ—

፳፩ እና የትኛውንም በረከት ከእግዚአብሔር ስናገኝ፣ ሁሉም ነገር በተመረኮዘበት ለዚያ ህግ ታዛዥ በመሆን ነው።

፳፪ ᵐአብ እንደ ሰው ሊዳሰስ እና ሊጨበጥ የሚችል የስጋ እና አጥንት ᵃአካል አለው፤ ወልድም ደግሞ እንዲሁ ነው፣ ነገር ግን ᶜመንፈስ ቅዱስ የስጋ እና አጥንት አካል የለውም፣ ነገር ግን የመንፈስ አካል ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ፣ መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ለመኖር ባልቻለ ነበር።

፳፫ ሰው ᵐመንፈስ ቅዱስን ሊቀበል ይችላል፤ እና በላዩም ሊወርድበትና አብሮትም ላይቆይ ይችላል።

፲፩ ᵐ ኢሳ. ፳፪፡፪።
ᵃ ራዕ. ፪፡፲፯።
፲፪ ᵐ ት. እና ቃ. ፴፳፡፳፤ ፵፭፡፳፫።
ᵃ ት. እና ቃ. ፹፯፡፩–፭።
፲፬ ᵐ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
፲፰ ᵐ ቅ.መ.መ. እውቀተኛነት፣ እውቀተኛዎች።
ᵃ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
፲፱ ᵐ ቅ.መ.መ. ትጋት።
ᵃ ቅ.መ.መ. ታዛዥነት፣ ታዛዥ፣ መታዘዝ።
ᶜ ቅ.መ.መ. እውቀት።
ᵐ አልማ ፲፪፡፱፤ ፴–፴፩።
፳ ᵐ ቅ.መ.መ. ቅድመ ምድራዊ ህይወት።
ᵃ ዘዳግ. ፲፩፡፳፭–፳፰፤ ት. እና ቃ. ፲፴፪፡፭። ቅ.መ.መ. መባረክ፣ የተባረከ፣ በረከት።
ᶜ ት. እና ቃ. ፹፪፡፲።
፳፪ ᵐ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ።
ᵃ የሐዋ. ፲፯፡፳፱።
ᶜ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
፳፫ ᵐ ቅ.መ.መ. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ።

ክፍል ፤፱፩

በግንቦት ፲፯ እና ፲፯፣ ፲፰፤፱፯፲ (እ.አ.አ.) በራመስ ኢለኖይ ውስጥ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተሰጡ መመሪያዎች።

፩–፬፣ የሰለስቲያል ጋብቻ ከፍ ባለው ሰማይ ዘለአለማዊ ክብር ለማግኘት አስፈላጊ ነው፤ ፭–፮፣ ሰዎች ለዘለአለም ህይወት እንዴት እንደታተሙ ተገልጿል፤ ፯–፳፣ መንፈስ ሁሉ ግዝፈት ያለው ነው።

፩ ᵐበሰለስቲያል ክብር ውስጥ ሶስት ሰማያት ወይም ደረጃዎች አሉ፤

፪ ᵐከፍተኛውን ለማግኘት፣ ሰው ወደ እዚህ የክህነት ስርዓት መግባት አለበት [ይህም ᵃአዲስ እና ዘለአለማዊ የጋብቻ ቃል ኪዳን ማለት ነው]፤

፫ እና ይህን ባያደርግ፣ ሊያገኘው አይችልም።

፬ ወደሌሎቹ ለመግባት ይችላል፣ ነገር ግን ያም የሚያደርገው መጨረሻው መንግስቱ ነው፤ ᵐተጨማሪም ሊያገኝ አይችልም።

፭ [ግንቦት ፲፯፣ ፲፰፤፱፯፲ (እ.አ.አ.)]። በተጨማሪ እርግጠኛ ᵐየትንቢት ቃል ማለት በራዕይ እና በትንቢት መንፈስ፣ በቅዱስ የክህነት ሀይል አማካይነት፣ ሰው ᵃለዘለአለም ህይወት ᶜእንደታተመ አውቋል ማለት ነው።

፮ ሰው ᵐበድንቁርና ᵃይድን ዘንድ አይችልም።

፯ ስለዚህ፣ ህልውና የሌለው ህልው ነገር የሚባል ነገር የለም። ᵐመንፈስ ሁሉ ህልውና ያለው ነው፣ ነገር ግን ይህም የጠራ እና ንጹህ ነው፣ እና ሰውም ሊለየው የሚችለው ᵃበነጹ አይኖች ብቻ ነው፤

፰ እናየውም ዘንድ አይቻለንም፤ ነገር ግን ሰውነቶቻችን ሲነጹ ግዝፈት ያለው እንደ ሆነ ሁሉ እናያለን።

ክፍል ፤፱፪

በናቩ ኢለኖይ ውስጥ በሐምሌ ፲፪፣ ፲፱፤፱፯፲ (እ.አ.አ.) የተመዘገበው፣ ስለአዲስ እና ዘለአለማዊ ቃል ኪዳን፣ በተጨማሪም የጋብቻ ቃል ኪዳን ዘለአለማዊ ነትን እና ደግሞም ከአንድ በላይ ሚስቶችን ስለማግባት መሰረታዊ መርሆ በሚ መለከት በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ምንም እንኳን ይህ ራዕይ በ፲፰፤፱፯፲ (እ.አ.አ.) የተመዘገበ ቢሆንም፣ ከዚህ ራዕይ ጋር የተገናኙ አንዳንድ መርሆች ለነቢዩ ከ፲፰፤፱፯፩ (እ.አ.አ.) መጀመሪያ ጀምሮ ታውቀው ነበር። አስተዳደሪያዊ አዋጅ ፩ን ተመልከቱ።

፩–፯፣ ዘለአለማዊ ክብር የሚገኘው በአዲስ እና ዘለአለማዊ ቃል ኪዳን ነው፤ ፯–፲፩፣ የዚህ ቃል ኪዳን ምልክት እና ቅድመ ሁኔታዎች ተሰጥተዋል፤ ፲፪–፳፣ ሰለስቲ

፤፱፩ ፩ ሀ ት. እና ቃ. ፫፤ ፫።
ቅ.መ.መ. የሰለስቲያል ክብር።
፪ ሀ ት. እና ቃ. ፤፱፩፤ ፩–፳፩።
ቅ.መ.መ. ከፍተኛነት።
ለ ቅ.መ.መ. ጋብቻ፣ መጋባት—አዲስ እና ዘለአለማዊ የጋብቻ ቃል ኪዳን።
፩ ሀ ት. እና ቃ. ፤፱፩፤ ፲፤–፲፯።
፭ ሀ ፪ ጴጥ. ፩፡ ፲፱።
ቅ.መ.መ. መጠራት እና መመረጥ።
ለ ቅ.መ.መ. የዘለዓለም ህይወት።
ሐ ት. እና ቃ. ፳፰፤ ፲፪፤ ፲፫፳፡ ፩።
ቅ.መ.መ. ማተም፣ ማስተሳሰር።
፯ ሀ ት. እና ቃ. ፤፲፯፡ ፣፲፱–፤።
ለ ቅ.መ.መ. ደህንነት።
፣ ሀ ቅ.መ.መ. መንፈስ።
ለ ት. እና ቃ. ፫፤ ፲፪፤ ፣፲፯፤ ፣፲፯፤ ሙሴ ፩፡ ፲፩።

ያል ጋብቻ እና የቤተሰብ ስብስብ ቀጣይ ነት ሰዎች አማልክት እንዲሆኑ ያስችላቸ ዋል፤ ፲፩–፲፫፣ ቀጭኑ እና ጠባቡ መን ገድ ወደዘለአለም ህይወት ይመራል፤ ፲፬–፲፯፣ መንፈስ ቅዱስን መስደብ በሚመለ ከት ህግ ተሰጠ፤ ፲፰–፴፪፣ የዘለአለማዊ እድገት እና ዘለአለማዊ ክብር ቃል ኪዳን ለሁሉም ዘመን ነቢያት እና ቅዱሳን ተደ ርገዋል፤ ፴–፴፯፣ ጆሴፍ ስሚዝ በምድር ላይ እና በሰማይ ውስጥ ለማሰር እና ለማ ተም ሀይል ተሰጠው፤ ፴፰–፴፣ ጌታ በእ ርሱ ላይ ዘለአለማዊ ክብር አተመበት፤ ፴፩–፴፯፣ ኤማ ስሚዝ ታማኝ እና እው ነተኛ እንድትሆን ተመከረች፤ ፴፰–፴፤፣ ከአንድ በላይ የሆኑ ሚስቶችን ስለማግባት የሚመሩ ህግጋት ተሰጥተዋል።

፩ በእውነትም ለአንተ አገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ጌታ እንዲህ ይላል፣ እኔ ጌታ አገል ጋዮቼን አብርሐምን፣ ይስሀቅን፣ እና ያዕ ቆብን፣ ደግሞም ሙሴን፣ ዳዊትን፣ እና ሰለሞንን ብዙ ᵐሚስቶችና ዕቁባቶች የነበራ ቸውን መሰረታዊ መርሆች እና ትምህርቶ ችን በሚመለከት እንዴት ከጥፋት ነጻ እን ዳደረኳቸው እንዲገባህ እና ለማወቅ ከእጄ እንደጠየከኝ—

፪ እነሆ፣ እና አስተውል፣ እኔ ጌታ አምላ ክህ ነኝ፣ እና ይህን ጉዳይ በሚነካም መል ስን እሰጥሀለሁ።

፫ ስለዚህ፣ ልሰጥህ ያሉትን መመሪያዎች ለመቀበል እና ለማክበር ልብህን ᵐአዘጋጅ፤ ይህ ህግ ለተገለጠላቸው ሁሉ ይህን ማክበር አለባቸውና።

፬ እነሆ፣ አዲስ እና ዘለአለማዊ ᵐቃል ኪዳን ገልጬላችኋለሁና፤ እና ይህን ቃል ኪዳን ካልኖራችሁበት፣ ከዚያ ᵃየተኮነ ናችሁ ናችሁ፣ ማንም ይህን ቃል ኪዳን ᵃሊቃወምና እና ወደ ክብሬ ይገባ ዘንድ አይችልምና።

፭ ከእጄ በረከት የሚያገኙም ለዚያ ᵐበረ ከት የተመደበውን ᵃህግና አለም ከመመስ ረቷም በፊት በስራ ላይ የዋሉትን ቅድመ ሁኔታ ሊኖሩባቸው ያስፈልጋቸዋልና።

፮ እና ᵐአዲስ እና ዘለአለማዊ ቃል ኪዳንን በሚመለከት፣ በስራ ላይ የዋለው ᵃለክብሬ ሙላት ነበር፤ እና ይህን ሙላት የሚቀበል በህጉ ይኑር እና መኖርም አለበት፣ ወይም ይኮነናል፣ ይላል ጌታ አምላክ።

፯ እና እውነት እላችኋለሁ፣ የዚህ ህግ ቅድመ ᵐሁኔታዎች እነዚህ ናቸው፥ በተቀ ባው፣ ለጊዜ እና ለዘለአለም፣ በዚህ ምድር ይህን ሀይል እንዲይዝ በመደብኩት (እና አገልጋዬ ጆሴፍን ይህን ሀይል በመጨረሻ ቀናት እንዲይዝ መድቤአለሁ እና የዚህ ክህነት ሀይል እና ᵃቁልፎች ይሰጠው ዘንድ የተገባ ከአንድ በላይ የለም) በእኔ በተቀባው በኩል ᵃበራዕይ እና በትዕዛዝ እና ከሁሉም በላይ በሆነ ᵐየቅዱስ ተስፋ መንፈስ ያል ተሰሩ፣ ያልገቡና ᵐያልታተሙ ቃል ኪዳ ናት፣ ስምምነቶች፣ የተፈረመባቸው መረ ጃዎች፣ ግዴታዎች፣ ᶜመሀላዎች፣ ስዕለ ቶች፣ ግንኙነቶች፣ ተባባሪነቶች፣ ወይም የሚጠበቅባቸው፣ በሙታን ትንሳኤ እና በኋላም ሁሉም ፍቱንነት፣ መልካምነት፣ ወይም ሀይል አይኖራቸውም፤ ለዚህም ውጤት ያልተገቡ ስምምነቶች ሰዎች በሞቱ ጊዜ መጨረሻው ይሆናል።

፰ እነሆ፣ ቤቴ የስርዓት ቤት ነው፣ ይላል ጌታ አምላክ፣ እና የግራ መግባት ቤት አይ ደለም።

፤፱፪ ፩ ሀ ት. እና ቃ. ፤፱፪፡፩፣ ፴፬፣ ፴፯–፴፱። ቅ.መ.መ. ጋብቻ፣ መጋባት—ከአንድ ሚስት በላይ ማግባት።
፫ ሀ ት. እና ቃ. ፳፱፡፳፣ ፶፣ ፶፮፡፯፣ ፹፡፩። ፬ ሀ ቅ.መ.መ. ቃል ኪዳን።
ለ ቅ.መ.መ. ኩነኔ።
ሐ ት. እና ቃ. ፤፱፩፡፩–፬።
፭ ሀ ት. እና ቃ. ፤፱፡፳–፳፩።
ለ ቅ.መ.መ. ህግ።
፮ ሀ ት. እና ቃ. ፳፮፡፪። ቅ.መ.መ. አዲስ እና የዘለአለም ቃል ኪዳን።
ለ ት. እና ቃ. ፫፮፡፫፣ ፲፪–፲፮። ቅ.መ.መ. የሰለስቲያል ክብር።
፯ ሀ ት. እና ቃ. ፲፫፡፲፣ ፴፰–፴፱።
ለ ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
ሐ ቅ.መ.መ. ራዕይ።
መ ቅ.መ.መ. ቅዱስ የተስፋ መንፈስ።
ሠ ቅ.መ.መ. ማተም፣ ማስተሳሰር።
ረ ቅ.መ.መ. መሀላ።

፱ በስሜ ያልተደረጉትን ᐟመስዋዕቶችን እቀበላለሁን? ይላል ጌታ።

፲ ወይም ᐟያልመደብኩትን ከእጆቻችሁ እቀበላለሁን?

፲፩ እና እንዲሁም እኔ እና አባቴ ለእናንተ ከዚህ አለም በፊት ᐟእንደሾምነው፣ በህግ ካልሆነ በስተቀር፣ ይላል ጌታ፣ እመድብ ላችኋለሁን?

፲፪ እኔ ጌታ አምላካችሁ ነኝ፤ እና ይህን ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ—በእኔ እና ህጌ በሆ ነው በቃሌ በቀር ወደ አብ ᐟየሚመጣ የለም፣ ይላል ጌታ።

፲፫ እና በአለም ያለው ሁሉም ነገር፣ በሰ ዎችም፣ ዙፋናት ወይም በጌትነት ወይም በአለቅነት ወይም በሥልጣናት ስም ባላቸው ነገሮች የተመደበ ቢሆንም፣ ምንም ቢሆኑ፣ በእኔ ወይም በቃሌ ካልሆኑ ይጣላሉ፣ ይላል ጌታ፣ እና ሰዎች ከሞቱም በኋላ፣ ወይም በትንሳኤ ወይም በኋላም እንዲሁ ᐟአይቀ ሩም፣ ይላል ጌታ አምላካችሁ።

፲፬ የሚቀሩትም ማናቸውም ነገሮች በእኔ ናቸው፤ እና በእኔ ያልሆኑትም ማናቸውም ነገሮች ይናወጣሉ እናም ይደመሰሳሉ።

፲፭ ስለዚህ፣ ሰው በአለም ውስጥ ሚስት ᐟቢያገባ፣ እና በእኔ ወይም በቃሌ ባያገ ባት፣ እና በአለም እስካለም ድረስ ከእርሷ ጋር እና እርሷም ከእርሱ ጋር ቃል ኪዳን ቢገቡ፣ ሲሞቱና ከአለም ሲለዩ ቃል ኪዳ ናቸውና ጋብቻቸው ሀይል አይኖራቸውም፤ ስለዚህ፣ ከአለም ሲለዩ በምንም ህግ አይ ታሰሩም።

፲፮ ስለዚህ፣ ከአለም ሲለዩ ᐟአያገቡም ወይም አይጋቡምም፤ ነገር ግን በሰማይ ውስጥ እንደ ᐟመላእክት ይመደባሉ፣ እነ ዚህም መላእክት ከዚህም በላይ፣ እና በክ ብርን በዘለአለም እድገት ከሁሉ ይልቅ ብቁ ለሆኑት ረጂ አገልጋዮች ናቸው።

፲፯ እነዚህ መላእክት በህጋቴ አልኖሩ ምና፤ ስለዚህ፣ ሊያድጉ አይችሉም፣ ነገር ግን ተለያይተው እና በብቸኝነት፣ ከፍ ሳይ ደረጉ፣ በዳኑበት ሁኔታ ዘለአለማዊ ክብር ሳይኖራቸው ይቆያሉ፤ እና ከዚያም ጊዜ ጀምሮ አማልክት አይደሉም፣ ነገር ግን ለዘ ለአለም የእግዚአብሔር መላእክት ናቸው።

፲፰ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ሰው ሚስት ቢያገባ፣ እና ለጊዜ እና ለዘለአለም ቃል ኪዳን ቢያደርግ፣ ያም ቃል ኪዳን በእኔ ወይም ህጌ በሆነው በቃሌ ባይጸና እና ለዚህ ሀይል በቀባሁት እና በመደብኩት በኩል በቅዱስ የተሰፋ መንፈስ ያልታተመ ቢሆን፣ ከዚያም ከዚህ አለም ሲለዩ ጋብ ቻቸው ተቀባይነት ወይም ሀይል የለውም፣ ምክንያቱም በእኔ ወይም በቃሌ አልተሳ ሰሩምና፣ ይላል ጌታ፤ ከአለም ሲለዩም በዚያም ተቀባይነት አያገኝም ምክንያቱም በዚያ ሊያልፏቸው የማይችሉ መላእክት እና አማልክት ተመድበዋልና፤ ስለዚህ ክብሬን መውረስ አይችሉም፤ ቤቴ የስር ዓት ቤት ነውና፣ ይላል ጌታ አምላክ።

፲፱ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ህጌ በሆነው በቃሌ እንዲሁም ᐟበአዲስ እና ዘለ አለማዊ ቃል ኪዳን ሰው ሚስትን ቢያ ገባ፣ እና ይህም በተቀባው፣ የዚህን ሀይል እና የዚህን ክህነት ᐟቁልፎች በመደብኩ ለት አማካይነት፣ በቅዱስ ᐟየተሰፋ መን ፈስ ᐟይታተማል፤ እናም ለእነርሱም እን ዲህ ይባላል—እናንተ በመጀመሪያው ትን ሳኤ ትመጣላችሁ፤ እና ከመጀመሪያው ትን ሳኤ በኋላም ቢሆን፣ በሚቀጥለው ትንሳኤ፤ እና ᐟዙፋናት፣ መንግስታት፣ ጌትነቶች፣

፱ ᐟ ሞሮኒ ፯፡፩–፭።
ቅ.መ.መ. መስዋዕት።
፲ ᐟ ዘሌዋ. ፳፪፡፳–፳፭፣
ሙሴ ፩፡፲፱–፳፫።
፲፩ ᐟ ት. እና ቃ. ፲፬፡፩–፩።
፲፪ ᐟ ዮሐ. ፲፡፱–፲፮።
፲፫ ᐟ ፫ ኔፊ ፳፯፡፣ ፲–፲፩።
፲፬ ᐟ ቅ.መ.መ. ጋብቻ፣ መጋባት።
፲፭ ᐟ ማቴ. ፳፪፡፳፫–፴፣
ማር. ፲፪፡፲፰–፳፭፣
ሉቃ. ፳፡፳፯–፴፮።
፲፮ ᐟ ቅ.መ.መ. መላእክት።
፲፱ ᐟ ቅ.መ.መ. ጋብቻ፣
መጋባት—አዲስ እና
ዘለአለማዊ የጋብቻ
ቃል ኪዳን።
፲፰ ᐟ ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
ሐ ት. እና ቃ. ፫፮፡፱–፲፣
ᐟ ፲፫፡፲–፲፩።
መ ቅ.መ.መ. ማተም፣
ማስተሳሰር።
ሠ ዘፀአ. ፲፱፡፩–፮፣
ራዕ. ፩፡፲፣ ፳፡፮፣
ት. እና ቃ. ፫፮፡፱፮፣
፫፰፡፲፩፣ ፲፳።

እና ሀይላት፣ አለቅነት፣ ሁሉንም ከፍታና
ዝቅታን ይወርሳሉ—ከዚያም በበጉ [ረ]የህይ
ወት መፅሀፍ ውስጥ ንጹህ ደም የማይፈስበት
ግድያን እንደማይፈፅም ይጻፋል፣ እና በቃል
ኪዳኔ ብትኖሩ፣ እና ንጹህ ደም የሚያፈስ
በትን ግድያ ባትፈጸሙ፣ በጊዜ እና በዘለ
አለም ሁሉ አገልጋዬ በእነርሱ ላይ የሚኖ
ረው ማንኛውም ነገሮች ሁሉ ይደረጉላቸ
ዋል፤ እና ከዚህ አለም ሲለዩም ሙሉ ሀይል
ያለው ይሆናል፤ እና በዚያ በተቀመጡት
በመላእክት እና አማልክት አልፈው፣ በራ
ሳቸው ላይ እንደታተሙት በሁሉም ነገሮች
ወደ [ሰ]ዘለአለማዊ ክብር እና ወደ ክብራቸው
ይሄዳሉ፣ ይህም ክብር ለዘለአለም የሙላት
እና ለዘራቸውም ቀጣይነት ያለው ይሆናል።

፳ ከዚያም እነርሱም አማልክት ይሆናሉ፣
ምክንያቱም መጨረሻ የላቸውምና፤ ስለ
ሚቀጥሉም፣ በዚህም ከዘለአለም ወደዘለ
አለም የሚኖሩ ይሆናሉ፤ ከዚያም ሁሉም
ነገሮች ለእነርሱ ተገዢ ስለሚሆኑ፣ ከሁሉም
በላይ ይሆናሉ። ከዚያም [ሀ]ሁሉም ሀይል ስለ
ሚኖራቸው፣ [ለ]አማልክት ይሆናሉ፣ እና
መላእክትም ተገዢ ይሆኑላቸዋል።

፳፩ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ [ሀ]በህጌ
ካልኖራችሁ በስተቀር ይህን ክብር አታገ
ኙም።

፳፪ ወደ ዘለአለማዊ ክብር እና ወደ ቀጣይ
[ሀ]ህይወት መቀጠል የሚወስደው ደጅ [ለ]የጠ
በበ፣ [ሐ]መንገዱም የቀጠነ ነውና፣ የሚያገ
ኙትም ጥቂቶች ናቸው፣ በዚህ አለም ስላ
ልተቀበላችሁኝ አታውቁኝም።

፳፫ ነገር ግን በዚህ አለም ብትቀበሉኝ፣
ከዚያም ታውቁኛላችሁ፣ እና ዘለአለማዊ
ክብራችሁንም ትቀበላላችሁ፤ እኔ [ሀ]ባለሁ
በት እናንተም ደግሞ ትሆናላችሁ።

፳፬ እውነተኛ እና የጥበብ አምላክ ብቻ
የሆነውንና [ሀ]የላከውንም ኢየሱስ ክርስቶ
ስን ያውቁ ዘንድ ይህች [ለ]የዘለአለም ሕይ
ወት ናት። እኔም እርሱ ነኝ። ስለዚህ ህጌን
ትቀበላላችሁ።

፳፭ ወደ [ሀ]ሞት የሚመራው ደጅ [ለ]ሰፊ፣
እናም መንገዱም የሰፋ ነውና፤ ወደ እር
ሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው፣ ምክንያ
ቱም [ሐ]አይቀበሉኝም ወይም በህጌም አይ
ኖሩምና።

፳፮ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣
ሰው በቃሌ መሰረት ሚስት ቢያገባ፣ እና
እኔም በመደብኩት መሰረት [ሀ]በቅዱስ የተ
ስፋ መንፈስ ቢታተሙ፣ እና እርሱ ወይም
እርሷ በአዲስ እና ዘለአለማዊ ቃል ኪዳን
ላይ ምንም ኃጢአት ወይም መተላለፍ እና
ሁሉንም አይነት መተላለፍ ባያደርጉ እና
ንጹህንም ደም ለማፍሰስ [ለ]ባይገድሉ፣ በመ
ጀመሪያው ትንሳኤ ይመጣሉ፣ እና ወደ ዘለ
አለማዊ ክብራቸውም ይገባሉ፤ ነገር ግን
በስጋቸው የወደቁ ይሆናሉ፣ እና እስከ
ቤዛም ቀን [ሐ]በሰይጣን እንዲጎሰሙ [መ]ይሰ
ጣሉ፣ ይላል ጌታ።

፳፯ መንፈስ ቅዱስን [ሀ]መሳደብ ግን በዚህ
ዓለም ቢሆን ወይም በሚመጣው [ለ]ስርየት
የለውም፣ በዚያም አዲስ እና ዘለአለማዊ
ቃል ኪዳኔን ከተቀበላችሁ በኋላ ንጹ

፲፱ ረ ቅ.መ.መ. የሕይወት መፅሐፍ።
ሰ ቅ.መ.መ. ከፍተኛነት።
፳ ሀ ት. እና ቃ. ፶፥፳፯–፳፱፤ ፸፮፥፺፬–፺፰፤ ፹፬፥፴፰–፴፱።
ለ ማቴ. ፳፭፥፳፩፤ ት. እና ቃ. ፳፱፥፲፪–፲፫፤ ፻፴፪፥፴፯። ቅ.መ.መ. ሰው፣ ሰዎች—የሰው እንደ እግዚአብሔር አይነት ለመሆን ያለው ችሎታ።
፳፩ ሀ ቅ.መ.መ. ህግ።
፳፪ ሀ ማቴ. ፯፥፲፫–፲፬፣ ፳፫፤ ፪ ኔፊ ፱፥፵፩፤ ፴፩፥፲፯–፳፩።
ለ ሉቃ. ፲፫፥፳፬፤ ፪ ኔፊ ፴፫፥፱፤ ሔለ. ፫፥፳፱–፴።
ሐ ት. እና ቃ. ፻፴፪፥፴–፴፩።
፳፫ ሀ ዮሐ. ፲፬፥፪–፫።
፳፬ ሀ ዮሐ. ፫፥፲፮–፲፯፤ ት. እና ቃ. ፵፱፥፭።
ለ ዮሐ. ፲፯፥፫። ቅ.መ.መ. የዘለዓለም ህይወት።
፳፭ ሀ ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ሞት።
ለ ማቴ. ፯፥፲፫–፲፬፤ ፫ ኔፊ ፲፬፥፲፫–፲፭።
ሐ ዮሐ. ፭፥፵፫።
፳፮ ሀ ቅ.መ.መ. ቅዱስ የተስፋ መንፈስ።
ለ አልማ ፴፱፥፭–፮።
ሐ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
መ ት. እና ቃ. ፹፪፥፳፩፤ ፻፬፥፱–፲።
፳፯ ሀ ቅ.መ.መ. መስደብ፤ ይቅርታ የሌለው ኃጢያት።
ለ ማቴ. ፲፪፥፴፩–፴፪፤ ዕብ. ፮፥፬–፮፤ ት. እና ቃ. ፸፮፥፴፩–፴፭። ቅ.መ.መ. የጥፋት ልጆች።

ህን ደም በማፍሰስ የምትገድሉበት፣ እና በሞቴም የምትስማሙበት ነው፤ እና በዚህ ህግ የማይኖር ማንም ወደ ክብሬ ሊገባ አይችልም፣ ነገር ግን [ሐ]ይኮነናል፣ ይላል ጌታ።

፳፰ እኔ ጌታ አምላክህ ነኝ፣ እና ለአንተም ከአለም ፍጥረት በፊት በእኔ እና በአባቴ እንደተመደበ፣ የቅዱስ ክህነቴን ህግ እሰጥሀለሁ።

፳፱ [ሀ]አብርሐም በራዕይ እና ትእዛዝ፣ በቃሌ የተቀበለውን ሁሉንም ነገሮች ተቀበለ፣ እና ወደ ዘለአለማዊ ክብሩም ገብቷል እና በዙፋኑም ተቀምጧል ይላል ጌታ።

፴ አብርሐም ስለዘሩ እና ስለወገብም ፍሬው በሚመለከት [ሀ]ቃል ኪዳንን ተቀበለ—ከእርሱም [ለ]ወገብ፣ በስምም ከአገልጋዬ ዮሴፍ የመጣህ ነህ—እነዚህም በአለም ውስጥ እስከሚገኑ ድረስ ይቀጥላሉ፤ እና አብርሐምን እና ዘሩን በሚመለከት፣ ከአለም ውጪም ይቀጥላሉ፤ በአለም ውስጥ እና ከአለም ውጪም እንደ [ሐ]ከዋክብት በዝተውም ይቀጥላሉ፤ ወይም፣ በባህር ዳር ያለን አሸዋ ብትቆጥርም እነርሱን ልትቆጥራቸው አትችልም።

፴፩ ይህም ቃል ኪዳን ያንተም ነው፣ ምክንያቱም አንተ [ሀ]ከአብርሐም ነህና፣ እና ቃል ኪዳኑም ለአብርሐም ተሰርቶ ነበርና፤ እና በዚህ ህግም የአባቴ ስራ ይቀጥል ዘንድ፣ በዚህም እራሱን ያከብር ዘንድ ነው።

፴፪ ስለዚህ ሂድ እና የአብርሐምን [ሀ]ስራዎች አድርግ፤ ወደህጌም ግባ እናም ትድናለህ።

፴፫ ነገር ግን ወደ ህጌ ባትገባ ለአብርሐም የተገባውን የአባቴን ቃል ኪዳን አትቀበልም።

፴፬ እግዚአብሔር አብርሐምን [ሀ]አዘዘው እና [ለ]ሳራ ለአብርሐም [ሐ]አጋርን ሚስት ትሆነው ዘንድ ሰጠችው። እና ይህን ለምን አደረገች? ምክንያቱም ይህም ህግ ነበር፤ እና ከአጋርም ብዙ ህዝብ ወጣ። ስለዚህ ይህም፣ ከሌሎች ነገሮች ጋር፣ ቃል ኪዳኖችን ያሟላ ነበር።

፴፭ ስለዚህ አብርሐም በኩነኔ ላይ ነበር? እውነት እላችኋለሁ፣ አልነበረም፤ እኔ ጌታ ይህን [ሀ]አዝዤአለሁና።

፴፮ አብርሐም ልጁን [ሀ]ይስሀቅን ለመስዋዕት እንዲያቀርብ [ለ]ታዝዞ ነበር፤ ይሁን እንጂ፣ [ሐ]አትግደል ተብሎ ተፅፎ ነበር። አብርሐም ግን እምቢ አላለም፣ እና ይህም [መ]እንደፅድቅ ተቆጠረለት።

፴፯ አብርሐም [ሀ]እቁባቶችን ተቀበለ፣ እና እነርሱም ልጆችን ወለዱለት፤ እና ይህም ለእርሱ እንደፅድቅ ተቆጥሮለታል፣ ምክንያቱም ለእርሱ ተሰጥተዋልና፣ እና በህጌም ኖሯል፤ ይስሀቅ እና [ለ]ያዕቆብም ከታዘዟቸው ነገሮች በስተቀር ምንም ሌላ ነገርን አላደረጉም፤ እና ከታዘዙትም ነገር ውጪ ምንም ሌላ ነገርን ስላላደረጉ፣ በቃል ኪዳኖች መሰረት [ሐ]ወደ ዘለአለማዊ ክብራቸው ገብተዋል፣ እና በዙፋናትም ተቀምጠዋል፣ እና መላእክት ሳይሆኑ አማልክት ናቸው።

፴፰ [ሀ]ዳዊትም [ለ]ብዙ ሚስቶች እና እቁባቶችን ተቀበለ፣ እና ከፍጥረት መጀመሪያ እስከዚህ ጊዜ ድረስ አገልጋዮቼም ሰለሞን እና ሙሴ፣ እና ብዙ ሌሎች አገልጋዮቼም

፳፯ሐ ቅ.መ.መ. ኩነኔ።
፳፱ሀ ቅ.መ.መ. አብርሐም።
፴ሀ ዘፍጥ. ፲፪፥ ፩–፫፤ ፲፫፥ ፲፮።
ቅ.መ.መ. አብርሐም—
የአብርሐም ዘር፤
የአብርሐም ቃል ኪዳን።
ለ ፪ ኔፊ ፫፥ ፮–፲፮።
ሐ ዘፍጥ. ፲፭፥ ፭፤ ፳፪፥ ፲፯።
፴፩ሀ ት. እና ቃ. ፹፮፥ ፰–
፲፩፤ ፻፲፥ ፲፪።
፴፪ሀ ዮሐ. ፰፥ ፴፱፤
አልማ ፭፥ ፳፬–፳፭።
፴፬ሀ ዘፍጥ. ፲፮፥ ፩–፫።
ለ ቅ.መ.መ. ሳራ።
ሐ ዘፍጥ. ፳፭፥ ፲፪–፲፰።
ቅ.መ.መ. አጋር።
፴፭ሀ ያዕቆ. ፪፥ ፳፬–፴።
፴፮ሀ ቅ.መ.መ. ይስሐቅ።
ለ ዘፍጥ. ፳፪፥ ፪–፲፪።
ሐ ዘፀአ. ፳፥ ፲፫።
መ ያዕቆ. ፬፥ ፭።
ቅ.መ.መ. ጻድቅ፣ ጽድቅ።
፴፯ሀ ይህም ሌሎች ሚስቶች ማለት
ነው። ዘፍጥ. ፳፭፥ ፭–፮።
ለ ዘፍጥ. ፴፥ ፩–፬፤
ት. እና ቃ. ፻፴፫፥ ፶፭።
ቅ.መ.መ. ያዕቆብ፣
የይስሐቅ ልጅ።
ሐ ቅ.መ.መ. ሰው፣ ሰዎች—
የሰው እንደ እግዚአብሔር
አይነት ለመሆን ያለው
ችሎታ፤
ከፍተኛነት።
፴፰ሀ ቅ.መ.መ. ዳዊት።
ለ ፩ ሳሙ. ፳፭፥ ፵፪–፵፫፤
፪ ሳሙ. ፭፥ ፲፫፤
፩ ነገሥ. ፲፩፥ ፩–፫።

ደግመው ተቀበሉ፤ እና ከእኔም ዘንድ ካል ተቀበሏቸው ነገሮች በስተቀር፣ በምንም ኃጢአትን አልሰሩም።

፸፭ የዳዊት ሚስቶች እና እቁባቶች በአገልጋዬ በናታን እጅ እጅ እና የዚህ ሀይል ᵇቁልፍ በተሰጣቸው በሌሎች ነቢያት እጅ አማካይነት ለእርሱ ᵃየተሰጡት ከእኔ ዘንድ ነበር፤ እና ᶜከኦርዮ እና ሚስቱ ጉዳይ በስተቀር በእነዚህ ነገሮች በእኔ ላይ ምንም ኃጢአት አልሰራም፤ ስለዚህ ከዘለአለማዊ ክብሩም ወድቋል፣ እና የድርሻውንም ተቀብሏል፤ እና እነዚህንም ከዚህ አለም ውጪ አይወርሳቸውም፣ ለሌላ ᵐሰጥቻቸዋለሁና፣ ይላል ጌታ።

፸፮ እኔ ጌታ አምላካችሁ ነኝ፣ እና ለአንተ አገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ሁሉንም ነገሮች ᵇዳግም ትመልስ ዘንድ ሀላፊነት ሰጥቼሀለሁ። ያሻህንን ጠይቅ፣ እና በቃሌም መሰረት ይሰጥሀል።

፸፯ እና ስለ ማመንዘር ስለጠየቅህ፣ እውነት፣ እውነት እልሀለሁ፣ ሰው በአዲስ እና ዘለአለማዊ ቃል ኪዳን ሚስትን ቢቀበል፣ እና እርሷም በቅዱስ ቅባት ካልመደብኩላት ከሌላ ሰው ጋር ብትገኝ፣ አመንዝራለች፣ እና ትጠፋለች።

፸፰ በአዲስ እና ዘለአለማዊ ቃል ኪዳን ውስጥ ካልሆነች፣ እና ከሌላ ሰውም ጋር ብትሆን፣ ᵇአመንዝራለች።

፸፱ እና ባሏ ከሌላ ሴት ጋር ቢሆን፣ እና ᵇበመሀላም ላይ ቢሆን፣ መሀላውን ሰብሯል እና አመንዝሯል።

፹ እና እርሷ ካላመነዘረች፣ ነገር ግን ንጹህ ብትሆንና መሀላዋን ባትሰብር፣ እና ብታውቅም፣ እና እኔም ለአንተ ለአገልጋዬ ጆሴፍ ብትገልጥልህ፣ ከዚያም በቅዱስ ክህነት ስልጣን ሀይል መሰረት እርሷን ለመውሰድ እና ላላመነዘረው፣ ነገር ግን ᵇታማኝ ለሆነው ትሰጥ ዘንድ ሀይል አለህ፤ እርሱ በብዙዎች ላይ ገዢ ይሆናልና።

፹፩ የክህነትን ᵇቁልፎችና ሀይል በላይህ አድርጌአለሁ፤ በዚህም ሁሉንም ነገሮች ᵃዳግም እመልሳለሁ፤ በጊዜውም ሁሉንም ነገሮች አሳውቅሀለሁ።

፹፪ እና እውነት፣ እውነት እልሀለሁ፣ በምድር ᵇየምታትመው ሁሉ በሰማይ ይታተማል፤ እና በስሜ እና በቃሌ በምድር የምታሰረው ሁሉ በሰማያት ለዘለአለም ይታሰራል፣ ይላል ጌታ፤ በምድር ላይ ᵃየምትሰርዘው ኃጢአት ሁሉ በሰማይ ለዘለአለም ይሰረዛል፤ እና በምድር ላይ የምትይዘው ኃጢአት ሁሉ በሰማይ ለዘለአለም ይያዛል።

፹፫ ደግሜም፣ እውነት እላለሁ፣ የምትባርከውን ማንኛውንም እባርካለሁ፣ እና የምትረግመውን ማንኛውንም ᵇእረግማለሁ፣ ይላል ጌታ፤ እኔ ጌታ አምላክህ ነኝና።

፹፬ ደግሞም፣ አገልጋዬ ጆሴ እውነት እልሀለሁ፣ በምድር የምትሰጠው ማንኛውም ነገር፣ እና ለማንም በቃሌ እና በህጌ መሰረት ማንንም በምድር ላይ ምንም ብትሰጥ፣ ይህንም በእርግማን ሳይሆን በበረከት በሀይሌ እጎበኘዋለሁ፣ ይላል ጌታ፣ እና በምድር እና በሰማይ ያለኩኔ ይሆናል።

፹፭ እኔ ጌታ አምላክህ ነኝ፣ እና እስከ አለም ᵇመጨረሻ ድረስ እና ለዘለአለም ሁሉ ከአንተ ጋር እሆናለሁና፤ በእውነትም ᵃዘለአለማዊ ክብርህን ᶜአትምብሀለሁ፣ እና በአባቴ መንግስት ውስጥ ᵐከአባትህ አብርሐም ጋር ዙፋንን አዘጋጅልሀለሁና።

፸፭ ሀ ፪ ሳሙ. ፲፪፡ ፯–፰።
ለ ፪ ሳሙ. ፲፩፡ ፬፣ ፳፯፤ ፲፪፡ ፱፤ ፩ ነገሥ. ፲፭፡ ፭።
ቅ.መ.መ. ማመንዘር፤ ግድያ።
ሐ ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
መ ኤር. ፰፡ ፲።
፸ ሀ ጆስ.—ታ. ፩፡ ፴፫።
ቅ.መ.መ. የወንጌል ዳግም መመለስ።
፸፪ ሀ ት. እና ቃ. ፸፪፡ ፳፪–፳፯።

፸፫ ሀ ቅ.መ.መ. ቃል ኪዳን፤ ጋብቻ፣ መጋባት።
፸፬ ሀ ቅ.መ.መ. ንጹህነት።
፸፭ ሀ ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
ለ የሐዋ. ፫፡ ፳፩፤ ት. እና ቃ. ፹፯፡ ፲። ቅ.መ.መ. የወንጌል ዳግም መመለስ።
፸፮ ሀ ቅ.መ.መ. ማተም፣ ማስተሳሰር።
ለ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ስርየት።
፸፯ ሀ ዘፍጥ. ፲፪፡ ፩–፫፤ ት. እና ቃ. ፻፳፭፡ ፲፫።
፸፱ ሀ ማቴ. ፳፫፡ ፳።
ለ ት. እና ቃ. ፩፡ ፳፪። ቅ.መ.መ. መጠራት እና መመረጥ።
ሐ ት. እና ቃ. ፳፯፡ ፲፪።
መ ዘፍጥ. ፲፯፡ ፩–፳፤ ፪ ኔፊ ፳፡ ፪።

፪ እነሆ፣ [ሀ]መስዋዕቶችህን አይቻለሁ፣ እና ኃጢአቶችህንም ሁሉ እሰርያለሁ፤ ለነገርኩህ ለዚያ ታዛዥ በመሆን ያደረግኸውን መስዋዕትነት አይቻለሁ። ስለዚህ ሂድ፣ እና አብርሐም ልጁን ይስሀቅን ለመስዋዕት ያቀረበውን [ለ]እንደተቀበልኩኝ፣ የምታመልጥ በትንም መንገድ አዘጋጅቼአለሁ።

፪፩ እውነት እልሀለሁ፥ ለአንተ ለሚስትነት የሰጠሁህን ባሪያዬ ኤማ ስሚዝ ትረጋጋ ዘንድ እና እንድትሰጣትም ካዘዝኩህ በላይ እንዳትቀበል ትእዛዝን እሰጣታለሁ፤ ለአብርሐም እንዳደረግሁት፣ ለሁላችሁንም ለማረጋገጥ፣ እና ከእጆቻችሁ በቃል ኪዳን እና በመስዋዕት መስዋዕትን ለመጠየቅ ይህን አድርጌአለሁና ይላል ጌታ።

፪፪ እና አገልጋዬ [ሀ]ኤማ ስሚዝ ለአገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ የተሰጡትን፣ በፊቴ ሰጋ ያላቸውና ንጹህ የሆኑትን ነገሮች ሁሉ ትቀበል፤ እና ንጹህ ያልሆኑት፣ እና ንጹህ ነን የሚሉት፣ ይጠፋሉ፣ ይላል ጌታ አምላካችሁ።

፪፫ እኔ ጌታ አምላክሽ ነኝና፣ እና ድምጼንም አክብሪ፤ እና ለአገልጋዬ ጆሴፍም በብዙ ነገሮች ገዢ ይሆን ዘንድ ሰጥቼዋለሁ፤ በትንሽ ነገሮች [ሀ]ታማኝ ሆኗልና፣ እና ከዚህም ጊዜ ጀምሮ አበረታዋለሁ።

፪፬ እና ባሪያዬን ኤማ ስሚዝን ከአገልጋዬ ጆሴፍ ጋር እንድትኖር እና ከአገልጋዬ ጆሴፍ በስተቀር ከማንም ጋር እንዳትጣመር አዝዣታለሁ። ነገር ግን በዚህ ትእዛዝ ባትኖር ትጠፋለች፣ ይላል ጌታ፤ እኔ አምላክሽ ነኝ፣ እና በህጌም ባትኖር አጠፋታለሁ።

፪፭ ነገር ግን በዚህ ህግ ባትኖር፣ ከዚያም አገልጋዬ ጆሴፍ ሁሉንም ነገሮች፣ እንዲሁም እንዳለው፣ ለእርሷ ያድርግ፤ እና እኔም እባርከዋለሁ እናም አባዛዋለሁም እና ለእርሱም በዚህ አለም አባቶችና እናቶች፣ ወንድሞችና እህቶች፣ ቤቶችና መሬቶች፣ ሚስቶችና ልጆች [ሀ]በመቶ እጥፍ፣ እና በዘለአለምም አለማት [ለ]የዘለአለም ህይወትን አክሊል እሰጠዋለሁ።

፪፮ ደግሞም፣ እውነት እላለሁ፣ ገረዴ አገልጋዬን ጆሴፍ ለተላለፋቸው ይቅርታ ትስጠው፤ እና ከዚያም በእኔ ላይ በመተላለፍ ለተላለፈችው [ሀ]ይቅርታ ይሰጣታል፤ እና እኔ ጌታ አምላካችሁ እባርካታለሁ፣ እናም አባዛታለሁ፣ እና ልቧንም እንዲደሰት አደርጋለሁ።

፪፯ ደግሞም፣ እላለሁ፣ ጠላት መጥቶ እናም እንዳያጠፋውም፣ አገልጋዬ ጆሴፍ ንብረቱን ከእጆቹ አያውጣ፣ ሰይጣን ለማጥፋት [ሀ]ይፈልጋልና፤ እኔ ጌታ አምላክህ ነኝ፣ እና እርሱም አገልጋዬ ነውና፤ እና እነሆ፣ አስተውሉም፣ እኔ ከአባታችሁ አብርሐም ጋር፣ [ለ]እስከ ዘለአለማዊ ክብሩ እን ደነበርኩኝ፣ ከእርሱም ጋር ነኝ።

፪፰ አሁን፣ [ሀ]የክህነት ህግን በሚመለከት፣ ይህን የሚመለከቱ ብዙ ነገሮች አሉ።

፪፱ እውነት፣ ሰው በአባቴ እንደ [ሀ]አሮን በድምጼ፣ እና በላከኝም ድምፅ፣ ቢጠራ እና እነዚህንም የክህነት [ለ]ቁልፎች ባበረከት ለት፣ በስሜ፣ በህጌና በቃሌ ምንም ነገንር ቢያደርግ፣ ምንም ኃጢአትን አይሰራም፣ እና እኔም ከጥፋት ነጻ አደርገዋለሁ።

፳ ስለዚህ ማንም አገልጋዬ ጆሴፍን አያጥቃ፤ እኔ ከጥፋት ነጻ አደርገዋለሁና፤ ለተላለፋቸው ከእጆቹ የምጠብቃቸውን መስዋዕቶች ያደርጋልና፣ ይላል ጌታ አምላካችሁ።

፳፩ ደግሞም፣ የክህነት ህግን በሚመለከት—ማንም ሰው [ሀ]ድንግልን ቢያገባ፣ እና [ለ]ሌላን ለማግባት ፍላጎት ቢኖረው፣ እና የመጀመሪያዋም ፈቃዷን ብትሰጥ፣

፪ ሀ ቅ.መ.መ. መስዋዕት።
ለ ዘፍጥ. ፳፪፡፡–፲፫፣
ት. እና ቃ. ፻፲፡፡፳።
፪፪ ሀ ቅ.መ.መ. ስሚዝ፣ ኤማ ሄል።
፪፫ ሀ ማቴ. ፳፭፡፡፳፩፤
ት. እና ቃ. ፻፪፡፡፲፫።
፪፬ ሀ ማር. ፣፡፡ ፳፡፡–፴፩።
ለ ቅ.መ.መ. ቤተሰብ—
ዘለአለማዊ ቤተሰብ፤
የዘለዓለም ህይወት።
፪፮ ሀ ቅ.መ.መ. ይቅርታ ማድረግ።
፪፯ ሀ ማቴ. ፣፡ ፳፡፡።
ለ ቅ.መ.መ. ከፍተኛነት።
፪፡ ሀ ት. እና ቃ. ፸፬፡፡፲፬–፳፩።
ቅ.መ.መ. ክህነት።
፪፱ ሀ ዕብ. ፭፡፡፬።
ቅ.መ.መ. አሮን፣
የሙሴ ወንድም።
ለ ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
፳፩ ሀ ቅ.መ.መ. ድንግል።
ለ ኢ.ኢ. ፩።
ቅ.መ.መ. ጋብቻ፣
መጋባት—ከአንድ
ሚስት በላይ ማግባት።

እና ሁለተኛይቱን ቢያገባ፣ እና እነርሱም ድንግል ቢሆኑ፣ እና ለሌላም ሰው መሀላ ባይገቡ፣ እርሱም አያጠፋም፤ እርሱም አያመነዝርም ምክንያቱም ለእርሱ ተሰጥ ተውታልና፤ ከእርሱ በቀር ለማንም ካልሆኑት ጋር አያመነዝርምና።

፳፪ በዚህ ህግ አስር ድናግል ቢሰጡትም፣ ሊያመነዝር አይችልም፣ የእርሱ ናቸውና፣ እና ለእርሱም ተሰጥተውታልና፤ ስለዚህ አይጠፋም።

፳፫ ነገር ግን አንድ ወይም ከአስር ደና ግላን አንዷ ካገባች በኋላ ከሌላም ወንድ ጋር ብትሆን፣ አመንዝራለች እና ትጠፋለችም፤ እነርሱም የሰው በትእዛዜ መሰረት ነፍሳትን እንዲወልዱ፣ እና ከአለም መመስረት በፊት በአባቴ የተሰጠውን ቃል ኪዳን ለማሟላት፣ እና በዘለአለሙም አለማት ዘለአለማዊ ክብራቸው "እንዲበዛና ምድርን እንዲሞላ የተሰጡት ናቸውና፤ ይህም ይከበር ዘንድ የአባቴ ^ስራ የሚቀጥልበት ነውና።

፳፬ ደግሞም፣ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ የዚህን ሀይል ቁልፍ የያዘ ማንም ሰው ሚስት ቢኖረው፣ እና እነዚህን ነገሮች በሚመለከት የክህነቴን ህግ ቢያስተምራት፣ ከዚያም እርሷም ትመነው እናም ትደግፈው፣ ወይም ትጠፋለች፣ ይላል ጌታ አምላካችሁ፤ እኔ አጠፋታለሁና፤ ህጌን የሚቀበሉ እና በህጌም የሚኖሩትን ሁሉ አጎላቸዋለሁና።

፳፭ ስለዚህ፣ ስላላመነች እና በቃሌ መሰረት ስላልረዳችው፣ ይህን ህግ ባትቀበል፣ እኔ ጌታ የምሰጠውን ማንኛዎቹን ነገሮች ሁሉ ለመቀበል ይህም በእኔ ዘንድ እንደ ህግ ይሆናል፤ እና ከዚያም እርሷም ህግ ተላላፊ ትሆናለች፤ እና እርሱም አብርሐም አጋርን እንዲያገባ ባዘዝኩት ጊዜ ለአብራም በህጉ መሰረት ከደገፈችው ከሳራ የህግ ግዴታ ነጻ ነው።

፳፮ አሁንም፣ ይህን ህግ በሚመለከት፣ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ከዚህ በኋላ ተጨማሪን ነገር እገልጥላችኋለሁ፤ ስለዚህ፣ ለጊዜው ይህ ይብቃ። እነሆ፣ እኔ አልፋና ኦሜጋ ነኝ። አሜን።

ክፍል ፲፱

በሀዳር ፫፣ ፲፰፻፲፱ (እ.አ.አ.) በሀይረም ኦሀዮ ውስጥ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ይህን ራዕይ በማስተዋወቅ የጆሴፍ ስሚዝ ታሪክ እንደሚገልጸው፥ "በዚህ ጊዜ ሽማግሌዎች ወንጌሉን ለምድር ነዋሪዎች ስለመስበክ፣ እና መሰብሰብን በሚመለከት ብዙ ነገሮችን ለማወቅ ፈልገው ነበር፤ እና በእውነት ብርሀን ለመራመድ፣ እና ከበላይም ለመመራት፣ በሀዳር ፫፣ ፲፰፻፲፱ (እ.አ.አ.)፣ ጌታን ጠየቅሁ እና ይህን አስፈላጊ ራዕይ ተቀበልኩ።" ይህም ክፍል በትምህርት እና ቃል ኪዳን መፅሐፍ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደ ተጨማሪ ሆኖ ነበር እና በኋላም የክፍል ቁጥር ተመደበለት።

፩–፯፣ ቅዱሳን ለዳግም ምፅዓት እንዲዘጋጁ ታዝዘዋል፤ ፯–፲፯፣ ሁሉም ሰዎች ከባቢሎን እንዲሸሹ፣ ወደ ፅዮን እንዲመጡ፣ እና ለጌታም ታላቅ ቀን እንዲዘጋጁ ታዝዘዋል፤ ፲፯–፴፭፣ እርሱ በፅዮን ተራራ ላይ ይቆማል፣ ክፍለ አህጉራትም አንድ ምድር ይሆናሉ፣ እና የጠፉት የእስራኤል ነገዶች ይመለሳሉ፤ ፴፮–፴፣ ወንጌሉ በአለም እንዲሰበክ በጆሴፍ ስሚዝ በኩል ዳግም ተመልሷል፤ ፴፩–፴፩፣ ጌታ

በክፉዎች ላይ ለበቀል ይወርዳል፤ ፱፪–፱፯፣ የቤዛነቱም አመት ይሆናል፤ ፱፰–፫፷፩፣ ወንጌል ቅዱሳንን ለማዳን እና ክፉ ዎችንም ያጠፉ ዘንድ ተልኳል።

፩ የቤተክርስቲያኔ ህዝብ ሆይ፣ አድ ምጡ፣ ይላል ጌታ አምላ ካችሁ፣ እና እና ንተን በሚመለከት የጌታን ቃል ስሙ—

፪ ወደ ᐸቤተመቅደሱ በድንገት የሚመ ጣው ጌታ፤ አዎን፣ እግዚአብሔርን በእ ርሱ ህዝብ ላይ፣ እና በመካከላችሁ ላሉ ኃጢአተኞች ላይ ሁሉ ᐳለፍርድ እርግ ማን ይዞ በምድር ላይ የሚወርደው ጌታን አድምጡ።

፫ እግዚአብሔር የተቀደሰውን ክንዱን በአሕዛብ ሁሉ ፊት ᐸይገልጣልና፣ እና በምድር ዳርቻ የሚኖሩትም ሁሉ የአም ላካቸውን ᐳመድኃኒት ያያሉ።

፬ ስለዚህ ህዝቤ ሆይ፣ ተዘጋጁ፣ ተዘጋጁ፤ ራሳችሁን ቀድሱ፤ የቤተክርስቲያኔ ህዝብ ሆይ፣ እንድትቆዩ ያልታዘዛችሁት ሁሉ አብራችሁ በፅዮን ምድር ውስጥ ተሰብሰቡ።

፭ ᐸከባቢሎንም ውጡ። የጌታን ዕቃ የም ትሸከሙ ᐳንፁሀን ሁኑ።

፮ የክብር ስብሰባችሁን ጥሩ፣ እና አንዳ ችሁ ከሌላችሁ በየጊዜው ᐸተነጋገሩ። እና እያንዳንዱም ሰው የጌታን ስም ይጥራ።

፯ አዎን፣ ደግሞም እውነት እላችኋ ለሁ፣ የጌታ ድምፅ ለእናንተ የሚሆንበት ጊዜ መጥቷል፥ ከባቢሎን ውጡ፤ ᐸከአ ራቱ ነፋሳት፣ ከሰማያትም ዳርቻ እስከ ዳርቻው ከሀገሮች መካከል ᐳተሰብስባ ችሁ ውጡ።

፰ መጀመሪያ ወደ ᐸአህዛብ እና ከዚያም ወደ ᐳአይሁድ፣ ሁሉንም ሀገሮች እንዲ ጠሯቸው የቤተክርስቲያኔን ሽማግሌዎች ወደ ራቅ ሀገሮች፣ ወደ ባህር ᐸደሴቶች ᐳላኳቸው፤ ወደ ባዕድ ሀገሮችም ላኳ ቸው።

፱ እናም እነሆ እና አስተውሉ፣ ይህም ጨኸታቸው እና ለሁሉም ህዝብ የጌታ ድምፅ ነው፥ የህዝቤ ድንበር ይሰፋ ዘንድ፣ እና ᐸካስማዎቿም ይጠናከሩ ዘንድ፣ እና ፅዮንም በአካባቢው ባሉ ሀገራት ትጎለብት ዘንድ ወደ ᐳፅዮን ምድር ሂዱ።

፲ አዎን፣ ከሁሉም ህዝብ መካከል ጨኸቱ ይውጣ፥ ንቁ፣ እና ተነሱ እና ሙሽራው ንም ለመገናኘት ሂዱ፤ እነሆ እና አስተ ውሉ፣ ᐸሙሽራው ይመጣል፣ ትቀበሉትም ዘንድ ውጡ። ለጌታ ᐳታላቅ ቀንም ራሳች ሁን አዘጋጁ።

፲፩ ቀኒቱንና ሰዓቲቱን ᐸአታውቁምና እን ግዲህ ᐳንቁ።

፲፪ ከአህዛብ ᐸመካከል ያሉትም ወደ ᐳፅዮን ይሸሹ።

፲፫ እና ᐸየይሁዳ የሆኑትም ወደጌታ ᐳቤት ᐸተራራዎች ወደ ᐸኢየሩሳሌም ይሸሹ።

፲፬ ከሀገሮች መካከል፣ እንዲሁም ከባቢ ሎን፣ መንፈሳዊ ባቢሎን ከሆነው ከክፋት መካከል ውጡ።

፪፻፫ ፪ ሀ ሚል. ፫፡፩፣
ት. እና ቃ. ፴፯፡፳።
ለ ት. እና ቃ. ፩፡፴፯።
ቅ.መ.መ. ኢየሱስ
ክርስቶስ—ዳኛ።
፫ ሀ ኢሳ. ፶፪፡፲።
ለ ኢሳ. ፲፪፡፪፣ ፶፪፡፲።
ቅ.መ.መ. የቤዛነት ዕቅድ፤
ደህንነት።
፭ ሀ አልማ ፭፡፶፯፣
ት. እና ቃ. ፩፡፲፯።
ቅ.መ.መ. ባቢሎን፤
አለማዊነት።
ለ ፪ ጢሞ. ፪፡፳፩፣
፫ ኔፊ ፳፡፴፩፣
ት. እና ቃ. ፴፯፡፴፪።
ቅ.መ.መ. ንጹህ፣ ንጹህነት።
፯ ሀ ሚል. ፫፡፲፯–፲፰።
፲ ሀ ዘካ. ፪፡፭–፯፣
ማር. ፲፫፡፳፯።
ለ ት. እና ቃ. ፳፱፡፳።
ቅ.መ.መ. እስራኤል—
የእስራኤል መሰብሰብ።
፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. አህዛቦች።
ለ ቅ.መ.መ. አይሁዶች።
ሐ ኢሳ. ፲፩፡፲፩፣
፩ ኔፊ ፳፪፡፰፣
፪ ኔፊ ፲፡፲፣ ፳።
መ ቅ.መ.መ. የሚስዮን ስራ።
፲፪ ሀ ኢሳ. ፶፬፡፪።
ቅ.መ.መ. ካስማ።
ለ ቅ.መ.መ. ፅዮን።
፲፫ ሀ ማቴ. ፳፫፡፮፣
ት. እና ቃ. ፴፫፡፲፣ ፲፯–፲፰፣
፴፭፡፴፩–፴፪።
ቅ.መ.መ. ሙሽራ።
ለ ት. እና ቃ. ፩፡፲፪–፲፩።
፲፬ ሀ ት. እና ቃ. ፴፱፡፯።
ለ ማር. ፲፫፡፴፪–፴፯፣
ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፡፴፯፣ ፴፰።
፲፪ ሀ ት. እና ቃ. ፴፰፡፴፩፣ ፴፪።
ለ ቅ.መ.መ. ፅዮን።
፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. ይሁዳ፣
የያዕቆብ ልጅ።
ለ መዝ. ፻፳፪።
ሐ ኢሳ. ፪፡፩–፫፣
ሕዝ. ፴፯፡፳።
መ ቅ.መ.መ. ኢየሩሳሌም።

፲፭ ነገር ግን በእውነት ጌታ እንዲህ ይላል፣ ሽሽታችሁ ᵐበችኮላ አይሁን፣ ነገር ግን ሁሉም ነገሮች በፊታችሁ ይዘጋጁ፤ እና የሚሄደውም፣ ድንገተኛ ጥፋትም እንዳይ ደርስበት ወደኋላ ᵃአይመልከት።

፲፮ የምድር ነዋሪዎች ሁሉ፣ ᵐአድምጡ እና ስሙ። የቤተክርስቲያኔ ሽማግሌዎች የሆናችሁ በአንድነት አብራችሁ አድምጡ፣ እና የጌታንም ድምፅ ስሙ፤ ሁሉንም ሰዎች ይጣራልና፣ እና በየትኛውም ስፍራ ለሚ ገኙ ሰዎች ሁሉ ᵃንስሀ ይገቡ ዘንድ ያዝዛ ቸዋል።

፲፯ እነሆም፣ ጌታ አምላክ በሰማያት መካከል እንዲህ በማለት በመጮህ መል አክᵐ ልኳል፥ የጌታን መንገድ አዘጋጁ፣ እና ጥርጊያውንም ᵃቀና አድርጉ፣ ᵃየመምጣ ቱም ጊዜ ቀርቦአልና—

፲፰ ᵐበጉ ᵃበፅዮን ተራራ ሲቆም፣ እና ከእ ርሱም ጋር የአባቱ ስም በግምባራቸው የተ ጻፈላቸው ᵃመቶ አርባ አራት ሺህ ነበሩ።

፲፱ ስለዚህ፣ ᵐለሙሽራው ᵃምጻት ተዘ ጋጁ፤ ሂዱ፣ ከእርሱም ጋር ለመገናኘት ሂዱ።

፳ እነሆም፣ በደብረ ዘይት ተራራና በታ ላቋ ባህር ላይ፣ እንዲሁም በታላቁ ጥልቅ፣ እና በባህር ደሴት ላይ፣ እና በፅዮን ምድር ላይ ᵐይቆማል።

፳፩ እና ᵐበፅዮንም ሆኖ ድምፁን ᵃከፍ አድርጎ ይጮኻል፣ እና ከኢየሩሳሌምም ይናገራል፣ እና ድምጹም በሁሉም ህዝብ መካከል ይሰማል፤

፳፪ ይህም ተራሮችን ᵐበሚሰብር፣ እና ሸለቆዎችን እንደሚለያይ በሚያደርግ እንደ ብዙ ውሀዎች ᵃድምፅና እንደ ታላቅ ᵃነጐ ድጓድ ድምፅ ይሰማል።

፳፫ ታላቁን ጥልቅ ያዝዘዋል፣ እና ይህም ወደ ሰሜን አገሮችም ይገፋል፣ እና ᵐደሴ ቶችም አንድ ምድር ይሆናሉ፤

፳፬ እና ᵐየኢየሩሳሌም ምድር እና የፅዮን ምድር ወደስፍራቸው ይመለ ሳሉ፣ እና ምድርም ᵃከመከፋፈልዋ ቀን አስቀድሞ እንደነበረችበትም አይነት ትሆናለች።

፳፭ እና ጌታ፣ እንዲሁም አዳኝ፣ በህ ዝቡ መካከል ይቆማል፣ እና ስጋ ለባሽ ሁሉ መካከል ᵐይነግሳል።

፳፮ እና ᵐበሰሜን ሀገሮች ያሉትም ጌታን ያስታውሳሉ፤ እና ነቢያቶቻቸውም ድም ጹን ይሰማሉ፣ እና ራሳቸውን ከዚህም በኋላ የሚታገሱ አይሆኑም፤ እና ድንጋ ይን ይመታሉ፣ እና በፊታቸውም በረዶ ዎች ይፈሳሉ።

፳፯ እና ᵐአውራ መንገድም በታላቁ ጥልቅ መካከል ይዘረጋል።

፳፰ ጠላቶቻቸውም ለእነርሱ እንደ አደን ይሆናሉ፣

፳፱ እና ፍሬ በማያፈራ ᵐበረሀ ውስጥም የህይወት ውሀ ምንጭ ይፈልቃል፤ እና

፲፭ ᵐ ኢሳ. ፶፪፡፲–፲፪፤ ት. እና ቃ. ፶፮፡፶፮። ᵃ ዘፍጥ. ፲፱፡፲፯፣ ፳፯፤ ሉቃ. ፱፡፳፪። ፲፯ ᵐ ት. እና ቃ. ፩፡፩–፯። ᵃ ቅ.መ.መ. መጻጸት፣ ንስሀ መግባት። ፲፯ ᵐ ት. እና ቃ. ፲፫፣ ፳፯፡፯–፳፡ ፹፡፳፡፶፪። ᵃ ኢሳ. ፵፡፫–፭። ᵃᵃ ሚል. ፫፡፩። ፲፰ ᵐ ራዕ. ፲፡፩ ᵃ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር በግ። ᵃ ት. እና ቃ. ፹፡፭። ᵃᵃ ራዕ. ፯፡፩–፱። ፲፱ ᵐ ቅ.መ.መ. ሙሽራ። ᵃ ማቴ. ፳፭፡፩–፲፫፣ ት. እና ቃ. ፴፫፡፲፯–፲፰፣ ፹፡፳፡፶፪። ᵃᵃ ዘካ. ፲፡፩፣ ት. እና ቃ. ፵፭፡፵፰–፶፫። ፳፩ ᵐ ኢሳ. ፪፡፪–፬። ᵃ ኢዩ. ፫፡፲፯፣ ዓሞ. ፩፡፪። ፳፪ ᵐ መዝ. ፳፯፡፲፰፣ ራዕ. ፲፡፪። ᵃ ሕዝ. ፴፫፡፪፣ ራዕ. ፩፡፲፭፣ ት. እና ቃ. ፴፣ ፫። ᵃᵃ መሳ. ፭፡፭፣ ኢሳ. ፵፡፬፣ ፳፡፩፣ ፩፣ ራዕ. ፲፯፡፳፣ ት. እና ቃ. ፵፱፡፳፫፣ ፸፡፲፡፶፪። ᵃᵃᵃ ኢሳ. ፴፭፡፩–፲፣ ፹፡፳፡፶፪። ᵃᵃᵃᵃ ራዕ. ፭፡፲፡ ᵃᵃᵃᵃᵃ ቅ.መ.መ. ኢየሩሳሌም። ᵃ ዘፍጥ. ፲፡፳፭። ᵃᵃᵃᵃᵃᵃ ቅ.መ.መ. ምድር— የምድር መከፋፈል። ᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—የክርስቶስ የአንድ ሺህ አመት ግዛት። ᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃ ኤር. ፲፮፡፲፰–፲፭፣ ት. እና ቃ. ፻፣ ፲፭። ᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃ ቅ.መ.መ. እስራኤል— የጠፉት የእስራኤል አስር ጎሳዎች። ᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃ ኢሳ. ፲፭፡፲፭–፲፯፣ ፪ ኔፊ ፳፭፡፲፯። ᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃᵃ ኢሳ. ፴፭፡፮–፯።

በጸሀይ የደረቀውም መሬት ዳግም የተ
ጠማ ምድር አይሆንም።
፳ እና የከበረ ሀብታቸውንም ወደ አገል
ጋዩ ᵐኤፍሬም ልጆች ያመጣሉ።
፳፩ እና የዘለአለም ᵐኮረብቶች ድንበሮ
ችም በፊታቸው ይንቀጠቀጣሉ።
፳፪ እና በዚያ፣ እንዲሁም በፅዮን ውስጥ፣
ይወድቃሉ እና በጌታ አገልጋዮች እጆ
ችም፣ እንዲሁም በኤፍሬም ልጆች፣ የክ
ብር አክሊል ይጎነጸፋሉ።
፳፫ እና እነርሱም በዘለአለም የደስታ
ᵐመዝሙር ይሞላሉ።
፳፬ እነሆ፣ ይህም በእስራኤል ᵐጎሳዎች
ላይ የዘለአለማዊው እግዚአብሔር በረከት፣
እና ᵃበኤፍሬም እና በባልንጀሮቹ ራስ ላይ
ዋጋ ያለው በረከት ነው።
፳፭ እና ᵐየይሁዳ ጎሳ ለሆኑትም፣ ከስቃ
ያቸው በኋላ ᵃበቅድስና በጌታ ፊት፣ በቀን
እና በማታ፣ ለዘለአለም፣ በፊቱ እንዲኖሩ
ይቀደሳሉ።
፳፮ አሁንም፣ በእውነት ጌታ እንዲህ
ይላል፣ የምድር ነዋሪዎች ሆይ፣ እነዚህ ነገ
ሮች በእናንተ መካከል የታወቁ ይሆኑ ዘንድ
የዘለአለም ᵐወንጌል ያለው፣ ለአንዳንዶች
የታየ እና ለሰውም ይህን የሰጠ፣ እና በምድር
ላይ ለሚኖሩት ለብዙዎች የሚታየው ᵃመል
አክ ከሰማይ መካከል እንዲበር ልኬአለሁ።
፳፯ እና ይህም ᵐወንጌል ᵃለእያንዳንዱ
ሕዝብ፣ ለነገድ፣ ቋንቋ፣ እና ወገንም ሁሉ
ᵐይሰበካል።
፳፰ እና የእግዚአብሔርም አገልጋዮች
በታላቅ ድምፅ፥ የፍርዱ ሰዓት ደርሶአልና
እግዚአብሔርን ፍሩ ክብርንም ስጡት በማ
ለት ይሄዳሉ፤
፳፱ እና ሰማይንና ምድርንም ባሕርንም
የውኃንም ምንጮች ለሠራው ᵐስገዱለት—
፴ በቀን እና በማታ የጌታን ስም በመጥ
ራት፥ ሰማያትን ᵐቀድደህ ብትወርድስ፣
ተራሮችም በፊትህ ቢናወጡስ በማለትም።
፴፩ እናም በራሳቸው ላይ መልስ ይሰ
ጣል፤ የጌታ መገኘት እሳት እንደሚያቀ
ልጥ እሳት፣ እና ውኃንም ᵐእንደሚያፈላ
እሳት ይሆናል።
፴፪ ጌታ ሆይ፣ ስምህ ለጠላቶችህ ይገለጥ
ዘንድ፣ እና አሕዛብም በፊትህ ይንቀጠቀጡ
ዘንድ ትወርዳለህ—
፴፫ ያልጠበቁትን የሚያስፈራውን ነገር
ባደረግህም ጊዜ፤
፴፬ አዎን፣ ወረድህ፣ እና ተራሮችም በፊ
ትህ ተንቀጠቀጡ፣ የሚደሰተውንና ጽድ
ቅን የሚያደርገውን በመንገዶችህም የሚ
ያስቡህን ᵐትገናኛቸዋለህ።
፴፭ እግዚአብሔር ሆይ፣ ሰዎች ከጥንት
ጀምሮ ᵐለሚጠብቁህ ᵃከምትሠራላቸው
ከአንተ በቀር ሌላ አምላክን አልሰሙም፣
በጆሮአቸውም አልተቀበሉም፣ ዓይንም
አላየችም።
፴፮ እና እንዲህም ይባላል፥ ከእግዚአብ
ሔር ዘንድ ከሰማይ የወረደው፣ ልብሱም
የቀላ፣ ከባሶራ ᵐየሚመጣ አለባበሱም
ያማረ፣ በጉልበቱስ ጽናት የሚራመድ ይህ
ᵃማን ነው?
፴፯ እርሱም ይላል፥ በጽድቅ የምናገር
ለማዳንም የምበረታ እኔ ነኝ።

፴ ᵐ ዘካ. ፲፣ ፭–፲፪።
ቅ.መ.መ. ኤፍሬም—
የኤፍሬም ጎሳ።
፴፩ ᵐ ዘፍጥ. ፴፱፡ ፳፯።
፴፫ ᵐ ኢሳ. ፴፭፡ ፲፣ ፶፩፡ ፲፩፣
ት. እና ቃ. ፳፯፡ ፲፩።
፴፬ ᵐ ቅ.መ.መ. እስራኤል—
የእስራኤል አስራ
ሁለት ጎሳዎች።
ᵃ ዘፍጥ. ፴፰፡ ፲፬–፳፣
፩ ዜና ፭፡ ፩–፪፣
ኤተር ፲፫፡ ፭–፲።
፴፭ ᵐ ቅ.መ.መ. ይሁዳ፣ የያዕቆብ
ልጅ—የይሁዳ ጎሳ።
ᵃ ቅ.መ.መ. ቅድስና።
፴፮ ᵐ ቅ.መ.መ. የወንጌል
ዳግም መመለስ።
ᵃ ራዕ. ፲፬፡ ፮–፯፣
ት. እና ቃ. ፳፡ ፩–፲፪።
፴፯ ᵐ ቅ.መ.መ. ወንጌል።
ᵃ ት. እና ቃ. ፴፪፡ ፶፳።
ᵃᵃ ቅ.መ.መ. መስበክ፣
የሚስዮን ስራ።
፴፱ ᵐ ቅ.መ.መ. ማምለክ።
፴ ᵐ ኢሳ. ፳፬፡ ፩–፪።
፴፩ ᵐ ኢዮብ ፴፩፡ ፴፩።
፴፪ ᵐ ፩ ተሰ. ፬፡ ፲፫–፲፯።
፴፫ ᵐ ሰቆ. ፫፡ ፳፫፣
፪ ኔፊ ፮፡ ፯፣ ፲፫።
ᵃ ኢሳ. ፳፬፡ ፬፣
፩ ቆሮ. ፪፡ ፱።
፴፮ ᵐ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ
ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
ᵃ ኢሳ. ፳፫፣ ፩–፪።

፶፰ እና ጌታም በልብሱ ᵐቀይ፣ እና ልብሱም ወይን በመጥመቂያ እንደሚረ ግጥ ሰው ልብስ ይሆናል።

፶፱ እና ከፊቱም ክብር ታላቅነት የተ ነሳ ᵐጸሀይ በእፍረት ፊቱን ይሸፍናል፣ እና ጨረቃም ብርሀኗን ትከለክላለች፣ እና ከዋ ክብትም ከስፍራቸው ይወረወራሉ።

፷ እና ድምጹም ይሰማል፥ ወይን መጭመቂያን ብቻዬን ᵐረግጫለሁ፥ እና በሁሉም ህዝብ ላይ ፍርድ አምጥቻለሁ፤ እና ማንም ሰው ከእኔ ጋር አልነበረም፤

፷፩ በቀኑ ጣዬ ረገጥኋቸው በመዓቴም ቀጠቀጥኋቸው፣ ደማቸውም በልብሴ ላይ ᵐተረጭቶአል፣ ልብሴንም ሁሉ አሣድፌ አለሁ፤ ይህም በልቤ የነበረው የምበቀል በት ቀን ነውና።

፷፪ አሁንም የምቤዥበትም ዓመት ደርሶ አል፤ እና የጌታቸውን አፍቃሪ ደግነትን እና በመልካምነቱም መሰረት፣ እናም በአፍቃሪ ደግነቱ መሰረት፣ በእነርሱ ላይ ስላፈሰሰው ሁሉ ለዘለአለም ይናገራሉ።

፷፫ ᵐበጭንቃቸው ሁሉ እርሱ ተጨነቀ። የፊቱን መልአክ አዳናቸው፤ ᵃበፍቅሩና በርኅራኄውም ᵇተቤዣቸው፣ በቀደመ ውም ዘመን ሁሉ አንሥቶ ተሸከማቸው፤

፷፬ አዎን፣ እና ᵐሔኖክ ደግሞም፣ እና ከእርሱም ጋር የነበሩት፤ ከእርሱ በፊት የነበሩት ነቢያት፤ እና ᵃኖህም ደግሞ፣ እና ከእርሱም በፊት የነበሩት፤ እና ᵇሙሴም፣ እና ከእርሱ በፊት የነበሩት፤

፷፭ ከሙሴ እስከ ኤልያስ፣ እና ከኤል ያስ ᵐበትንሳኤው ከክርስቶስ ጋር እስከ ነበ ረው ዮሐንስ፣ እና ቅዱስ ሐዋርያት፣ ከአ ብርሐም፣ ይስሀቅ፣ እና ያዕቆብ ጋር በበጉ ፊት ይሆናሉ።

፷፮ ᵐየቅዱሳን ᵃመቃብሮችም ᵇይከፈ ታሉ፤ እና ᶜበፅዮን ተራራ ላይ፣ እና በቅ ዱስቲቱ ከተማ ᵈአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ላይ ሲቆምም፣ እነርሱም ይመጣሉ እና በበጉም ᵉቀኝ ይቆማሉ፤ እና በቀን እና በማታ ለዘ ለአለም ᵃየበጉን ᵇመዝሙሮች ይዘምራሉ።

፷፯ እና ለዚህም ምክንያት ሰዎች የሚገለ ጡትን ᵐክብሮች ተካፋይ ይሆኑ ዘንድ፣ ጌታ ᵃየወንጌሉን ሙላት፣ ዘለአለማዊ ቃልኪዳ ኑን፣ በግልጽ እና በቀላል ምክንያቱን ላከ—

፷፰ በምድር ላይ ለሚመጡት ነገሮች ᵐደካማዎችን ለማዘጋጀት፣ እና ጥበበኞችን በሚያሳፍሩበት ቀን ለጌታ መልእክት፣ እና ᵃአነስተኛው ብርቱ ሕዝብ ይሆናል፣ እና ᵇሁለቱ አሥሩን ሺህ ያሸሻሉ።

፷፱ እና በመንፈሱ ኃይል ጌታ በአለም ደካማ ነገሮች አህዛብን ᵐይወቃል።

፸ እና ለዚህም ምክንያት እነዚህ ትእዛ ዛት ተሰጥተው ነበር፤ በተሰጧቸውም ቀን ከአለም ይሰውሯቸው ዘንድ ታዝዛው ነበር፣ ነገር ግን አሁን ወደ ሁሉም ᵐስጋ ለባሾች ᵃይሂዱ—

፸፩ እና ይህም ሁሉንም ስጋ ለባሽ በሚ ገዛው በጌታ አዕምሮ እና ፈቃድ መሰረት ነው።

፶፰ ᵃ ዘፍጥ. ፳፱፡፲፩–፲፪፤ ሉቃ. ፭፪፡፳፬፤ ራዕ. ፲፱፡፲፩–፲፭፤ ጆ.ስ.ት. ራዕ. ፲፱፡፲፩ (ተጨማሪ)፤ ሞዛያ ፫፡፯፤ ት. እና ቃ. ፲፱፡፲፰።

፶፱ ᵃ ኢሳ. ፲፫፡፲፣ ፳፬፡፭፣ ፳፰፡፲፣ ት. እና ቃ. ፴፭፡፴፪፤ ፹፡፳፯፡፹፯።

፷ ᵃ ኢሳ. ፳፫፡፪–፫፤ ት. እና ቃ. ፹፯፡፲፯፤ ፹፡፳፡፹፯።

፷፩ ᵃ ዘኤዋ. ፰፡፴።

፷፫ ᵃ ኢሳ. ፳፫፡፬–፱ ᵇ ቅ.መ.መ. ልግስና።

ሐ ቅ.መ.መ. ቤዛ፣ ማዳን፣ ቤዛነት።

፷፬ ᵃ ቅ.መ.መ. ሔኖክ።

ለ ቅ.መ.መ. ኖኅ፣ የመዕሐፍ ቅዱስ የአባቶች አለቃ።

ሐ ቅ.መ.መ. ሙሴ።

፷፭ ᵃ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።

፷፮ ᵃ ቅ.መ.መ. ቅዱሳን።

ለ ት. እና ቃ. ፷፱፡፲፫።

ሐ ት. እና ቃ. ፹፭፡፹፭–፹፮፣ ፹፡፳፡፲፯።

መ ኢሳ. ፷፱፡፳፣ ፳፫፡፲፣ ራዕ. ፲፱፡፩፣ ት. እና ቃ. ፫፡፲፯፣ ፹፡፳፡፪፡፪።

ሠ ቅ.መ.መ. አዲሲቱ ኢየሩሳሌም።

ረ ማቴ. ፳፭፡፲–፴፡፱።

ሰ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር በግ።

ሸ ራዕ. ፲፭፡፫፣ ት. እና ቃ. ፹፡፱፡፲፯–፲፪።

፷፯ ᵃ ቅ.መ.መ. የክብር ደረጃዎች።

ለ ቅ.መ.መ. ወንጌል።

፷፰ ᵃ ማቴ. ፲፩፡፳፭፣ ፩ ቆሮ. ፩፡፳፯፣ አልማ ፴፪፡፳፫፣ ፴፯፡፩–፯።

ለ ኢሳ. ፳፡፳፪።

ሐ ዘዳግ. ፴፪፡፳፱–፴።

፷፱ ᵃ ሚክ. ፬፡፲፩–፲፫።

፸ ᵃ ት. እና ቃ. ፩፡፪።

ለ ት. እና ቃ. ፲፡፣ ፲፯–፲፱።

፡፡፤ እና ᵐንስሀ ለሚገባው እና በጌታ ፊት ራሱን ᵃለሚቀድስም ᵐየዘለአለም ህይወ ትን ይሰጣል።

፡፡፣ እና የጌታን ድምፅ ᵐለማያደምጡም፣ ከህዝብ መካከል ᵃይቆረጡ ዘንድ፣ በነቢዩ ሙሴ የተጻፈውም ይፈጸማል።

፡፡፡ እና በነቢዩ ᵐሚልክያስ እንደተጻፈ ውም፥ እነሆ፣ እንደ ምድጃ እሳት የሚ ነድድ ᵃቀን ይመጣል፤ ትዕቢተኞችና ኃጢ አትን የሚሠሩ ሁሉ ገለባ ይሆናሉ፤ የሚ መጣውም ቀን ᵐያቃጥላቸዋልና፥ ሥርንና ቅርንጫፍንም አይተውላቸውም፣ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።

፡፡፡ ስለዚህ፣ ይህም ለእነርሱ የጌታ መልስ ይሆናል፥

፡፡፤ በዚያም ቀን ወደ ራሴ ስመጣ፣ በመካ ከላችሁ ማንም ᵐአልተቀበለኝም፣ እና ተሰ ድዳችሁም ነበር።

፡፡፣ በጠራሁስ ጊዜ የሚመልስ ማንም አልነበረም፤ ነገር ግን መታደግ እንዳል ችል ᵐእጄ አጭር አልሆነችም፣ ወይስ ለማ ዳን ᵃኃይል የለኝም።

፡፡፡ እነሆ፣ በገሠጽሁ ጊዜ ባሕርን ᵐአደ ርቃለሁ። ወንዞችንም ምድረበዳ አደርጋ ቸዋለሁ፤ ዓሦቻቸውም ይገማሉ በጥማ ትም ይሞታሉ።

፡፡፡ ሰማያትን ጥቁረት አለብሳቸዋለሁ፥ መጋረጃቸውንም ማቅ አደርጋለሁ።

፡፡ እና ᵐይህ ከእጄ ይሆንባችኋል—በጎ ዘን ትተኛላችሁ።

፡፡፤ እነሆ እና አስተውሉ፣ የሚያድና ችሁ ማንም የለም፤ ከሰማያት ስጠራችሁ ድምጼን አልታዘዛችሁበትምና፤ በአገል ጋዮቼ አላመናችሁም፣ እና ወደ እናንተም ᵐሲላኩ አልተቀበሏቸውም።

፡፡፣ ስለዚህ፣ ምስክሩን ᵐያትማሉ እና ህግ ንም ያስራሉ፣ እና ወደ ድቅድቅ ጭለማም ትጣላላችሁ።

፡፡፣ እነዚህም በድቅድቅ ጨለማ ይሄዳሉ፣ በዚያ ᵐልቅሶ፣ ሀዘንና፣ ጥርስ ማፏጨት ይሆናል።

፡፡፡ እነሆ ጌታ አምላካችሁ ይህን ተናግ ሯል። አሜን።

ክፍል ፤፡፡

በነሀሴ ፲፯፣ ፲፰፤፤፡ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ ኦሀዮ ውስጥ በነበረው በቤተክርስ ቲያኗ አጠቃላይ ስብሰባ ላይ በአንድ ድምፅ ምርጫ የተቀበሉት ስለመንግስት እና በአጠቃላይም ስለህግጋት የሚመለከት የእምነት እወጃ። ብዙ ቅዱሳን የትምህ ርት እና ቃል ኪዳን የመጀመሪያው ቅጂ ውስጥ እንዲኖር የቀረበውን ለማመዛዘን ተሰብስበው ነበር። በዚያም ጊዜ፣ የሚቀጥለው መግቢያ ለዚህ እወጃ ተሰጠው፥ "የምድር መንግስታትን እና አጠቃላይ ህግጋትን በሚመለከት ያለን እምነት የስ

፡፡፤ ሀ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣
ንስሀ መግባት።
ለ ት. እና ቃ. ፡፡፤፡–፡፡፡።
ቅ.መ.መ. ቅድስና።
ሐ ቅ.መ.መ. የዘለዓለም
ህይወት።
፡፡፣ ሀ ቅ.መ.መ. ማዳመጥ።
ለ የሐዋ. ፣፡–፡፡፣፡፣
፤ ኔፊ ፡፡፤፡–፡፡፤፡፣
፣ ኔፊ ፡፡፡፡፣ ፡፡፤፡፣ ፡፡፤፡፣
ት. እና ቃ. ፤፡፡፣
ጆ.ስ.—ታ. ፤፡–፡፡።

፡፡፡ ሀ ሚል. ፡፡፡–፤፡።
ቅ.መ.መ. ሚልክያስ።
ለ ጆ.ስ.—ታ. ፤፡–፡፡፤–፡፡፤።
ሐ ኢሳ. ፡፡፤፡–፣፡፤–፣፡፤፣
፤ ኔፊ ፡፡፤፡–፣፡፡፣
፣ ኔፊ ፡፡፤፡–፤፡፣
ት. እና ቃ. ፡፡፤፡–፡፡፡፡–፡፡፡።
ቅ.መ.መ. ምድር—
ምድርን ማፅዳት።
፡፡፤ ሀ ዮሐ. ፤፡–፣፤፤።
፡፡፣ ሀ ፤ ኔፊ ፡፡፡፡–፡፡፤።
ለ ኢሳ. ፤፡–፤፤፣
፤ ኔፊ ፡፡–፡፡።

፤ ኔፊ ፣–፤።
፡፡፡ ሀ ዘፀአ. ፣፡–፡፡፤፣
ኢ.ያ. ፣–፣፡–፣፣።
ሐ ሀ ኢሳ. ፤–፣፤፤
ሐ ሀ ፤ ዘና ፡፡፣፣–፣፣–፣፣፣
ኤር. ፡፡፡–፡–፣።
ሐ ሀ ኢሳ. ፡፡–፣፣–፡፡
ሐ ሀ ማቴ. ፡፡–፣፤–፣፤፣
ሉቃ. ፣፣–፡፡፡፣
ት. እና ቃ. ፣፤–፣።
ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ጭለማ፣
ሲያል።

ህተት ትርጉም ወይም የስህተት መረጃ እንዳይሆን፣ በዚህ መፅሀፍ መዝጊያ ላይ ይህን በሚመለከት አስተሳሰባችንን ማቅረብ ትክክለኛ እንደሆነ አስበናል።”

፩–፫፣ መንግስታት የህሊናን ነጻነት እና አምልኮን ይጠብቁ፤ ፬–፯፣ ሁሉም ሰዎች መንግስታቸውን መደገፍ እና ለህግም ታዛዥነት እና አክብሮት ሊኖራቸው ይገባል፤ ፰–፲፣ የሀይማኖት ህብረተሰቦች የህዝባዊ ሀይላት አይኑራቸው፤ ፲፩–፲፪፣ ሰዎች ራሳቸውን እና ንብረቶቻቸውን በመጠበቅ ከጥፋት ነጻ ይሆናሉ።

፩ [ሀ]መንግስታት እግዚአብሔር ለሰው [ለ]ጥቅም የመሰረታቸው እንደሆኑ እና ምናለን፤ እና እነዚህን በሚመለከትም፣ ለህብረተሰብ ጥቅም እና ደህንነት በሚሰሩት አማካይነት ህግጋትን እና እነርሱንም በሚያስተዳድሩ ሰዎችን በተጠያቂነት ይይዟቸዋል።

፪ ህግጋት ለእያንዳንዱ [ሐ]የህሊና [መ]ነጻነት ጥቅም፣ የንብረት መብትና ቁጥጥር፣ እና የህይወት [ሠ]ጥበቃን ለማግኘት ካልተመሰረቱ እና ተጥሰውም ካልተገኙ በስተቀር ምንም መንግስት በሰላም ለመኖር እንደማይችል እምነት አለን።

፫ መንግስታት ሁሉ እነዚህን ህግጋት ለማስከበር ህዝባዊ [ረ]ባለስልጣናት እና ዳኛዎች እንደሚያስፈልጋቸው እናምናለን፤ እና ህጉን በእኩልነት እና በፍትሀዊነት የሚያስተዳድሩም ሪፐብሊክ ከሆነ በህዝብ ድምፅ፣ ወይም በነገስታት ይፈለጉ፣ ይደገፉም።

፬ ሀይማኖት በእግዚአብሔር እንዲመሰረት እናምናለን፤ እና የሀይማኖታቸው አስተያየት የሌሎችን መብት እና ነጻነት እስካልጣሰ ድረስ፣ ይህን ለመጠቀምም ሰዎች ለእርሱ እና ለእርሱ ብቻ መልስን ይስጡ፤ ነገር ግን የሰዎች ህግ የሰዎችን ህሊና በማስተሳሰር የማምለክን ደንብ በማዘዝ ጣልቃ ለመግባት፣ ወይም የህዝባዊ ወይም የግል [ሰ]የአምልኮ መንገድን ለማዘዝ መብት እንዳላቸው አናምንም፤ ዳኞች ወንጀሎችን ያስቁሙ፣ ነገር ግን ህሊናን አይቆጣጠሩ፤ ወንጀለኛነትን ይቅጡ፣ ነገር ግን የነፍስን ነጻነት አይጨቁኑ።

፭ ሁሉም ሰዎች በሚኖሩባቸው መንግስታት ህግጋት የወረሱትን እና የማይነጠለውን መብቶቻቸውን የሚጠብቁላቸውን መንግስታት ለመቀበል እና ለመደገፍ ግዴታ እንዳላቸው እናምናለን፤ እና በእንደዚህ ከተጠበቁ ዜጎች ህዝብን [ሸ]ማሳመጽ እና መቃወም የሚጠበቅባቸው አይደለም፣ እና መቀጣትም ይገባቸዋል፤ እና መንግስታት ሁሉ የህዝብን ጥቅም በጥብቅ ለመያዝ የራሳቸውን ፍርድ በመልካምነት እንደሚያስቡት እንደዚህ አይነት ህግጋትን ለመስራት መብት አላቸው፤ በዚህም ጊዜ ግን፣ የህሊና ነጻነትን በቅድስና ይጠበቁ።

፮ እያንዳንዱም ሰው በተመደበለት ስፍራ ውስጥ መከበር እንደሚገባው፣ የዋሆችን ለመጠበቅ እና ወንጀለኞችን ለመቅጣት የተመደቡት መሪዎች እና ዳኛዎችም እንደዚህ መከበር እንደሚገባቸው እናምናለን፤ እና [ቀ]ለህግጋትም ሁሉም ሰዎች ክብር እና አክብሮትን ይስጡ፣ ካለእርሱም ስርዓት የለሽነት እና ሽብር ሰላምንና ስምምነትን ይሰጣሉ፤ የሰዎች ህግጋት የሚመሰረቱት እንደግለሰቦች እና እንደህዝቦች፣ በሰዎች እና ሰው መካከል፣ የምንፈልገውን ለመቆጣጠር በሚኖር አላማ ነው፤ እና ከሰማይ የተሰጡት መለኮታዊ ህግጋትም በመንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ መመሪያዎችን ለመጠቀም፣

፪፻፹፫ ፩ [ሀ] ት. እና ቃ. ፲፯፡፩–፲፤ እ.አ. ፩፡ ፲፪። [ለ] ቅ.መ.መ. መልስ መስጠት፣ ሂሳብ፣ ተጠያቂነት፣ ሀላፊነት። ፪ [ሀ] ቅ.መ.መ. ህሊና።

[ለ] ቅ.መ.መ. ነጻ ምርጫ። [ሐ] ት. እና ቃ. ፵፪፡ ፲፯–፲፱። ፫ [ሀ] ት. እና ቃ. ፶፯፡ ፯–፲። ፬ [ሀ] አልማ ፳፭፡ ፳፭–፳፪፣ እ.አ. ፩፡ ፲፩። ቅ.መ.መ. ማምለክ።

፭ [ሀ] እ.አ. ፩፡ ፲፪። ቅ.መ.መ. አመጽ። ፮ [ሀ] ት. እና ቃ. ፶፯፡ ፳፩፣ ፹፡ ፵፩። [ሀ] ቅ.መ.መ. ህሊና።

ለእምነትና ለአምልኮ፣ ሁለቱም በሰው እና በፈጣሪው ይመለሱ ዘንድ ነው።

፲ ገዢዎች፣ ስቴቶች፣ እና መንግስታት መብት እንዳላቸው፣ እና ዜጎች የሀይማኖት እምነታቸውን በነጻነት ለማምለክ እንዲጠ ብቋቸው ህግጋትን ለማሳለፍ የሚገባቸው እንደሆኑ እናምናለን፤ ነገር ግን ለህግጋት ትኩረትና ክብር እስከ ተሰጠ ድረስ እና እንደዚህ አይነቶቹ የሀይማኖት አስተያ የቶች ህዝብን ማሳመጽንና አድማን እንደ ጥፋት የማያዩ እስካልሆነ ድረስ በፍትህ ይህን መብት ለመውሰድ፣ ወይም በአስተ ያየታቸው እነዚህን ከህግ ውጪ ለማድረግ መብት እንዳላቸው አናምንም።

፲፩ ወንጀል መስራት እንደ ጥፋቱ መሰ ረት ᐟመቀጣት እንደሚገባው እናምናለን፤ መግደል፣ አገር መክዳት፣ መዝረፍ፣ መስ ረቅ፣ እና ሰላምን ማፍረስ፣ በሁሉም ሁኔ ታዎች፣ በወንጀልነታቸው መሰረት እና በሰዎች መካከል ጥፋት ለማድረግ ባላቸው ፍላጎት መሰረት ጥፋቱ በተደረገበት መን ግስት ህግጋት ይቀጡ፤ እና ለህዝባዊ ሰላም እና እርጋታ ሁሉም ሰዎች ወደፊት በመ ሄድ በመልካም ህግጋት ላይ የሚያጠፉትን ለቅጣት ለማምጣት ችሎታቸውን ይጠቀ ሙበት።

፲፪ የሀይማኖት ተፅእኖ ከህዝባዊ መንግስት ጋር በመቀላቀል አንድ የሀይማኖት ህብረተ ሰብን በማበረታታት እና ሌላን በመንፈሳዊ መብት ከህግ ወጪ በማድረግ፣ እና የእያን ዳንዱ አባላት መብቶችም እንደ ዜጋ መካዳ ቸው ትክክል እንደሆነ አናምንም።

፲፫ የፅድቅ ህብረተሰቦች ሁሉ አባሎቻቸው በሚረብሹበት ጊዜ በህብረተሰቦች መመሪ ያዎችና መቆጣጠሪያዎች መሰረት ለመቅ ጣት መብት እንዳላቸው እናምናለን፤ እነ ዚህ ቅጣቶች ለማህበርተኛነት እና ለመል ካም አቋም እስከሆነ ድረስ፤ ነገር ግን ምንም የሀይማኖት ህብረተሰብ ሰዎችን በንብረት ወይም በህይወት መብት ላይ፣ የዚህ አለም ቁሳቁሶችን ሊወስዱባቸው፣ ወይም በህይ ወታቸው ይሁን በሰውነታቸው ላይ አደጋን ሊያደርሱባቸው፣ ወይም ምንም የሰውነት ቅጣት በእነርሱ ላይ ለማድረግ ስልጣን እን ዳላቸው አናምንም። ከህብረተሰቦቻቸው ᐟይወገዙ ዘንድ ህብረታቸውን ለመውሰድ ብቻ ነው የሚችሉት።

፲፬ ሰዎች በህዝባዊ ህግ ለደረሰባቸው አግ ባብ ላልሆኑ ነገሮች እና ለቅሬታ፣ ለግል መጎሳቆልን፣ ወይም የንብረት ወይም የህ ሊና መብት መጣስን፣ እና እነዚህን ለመጠ በቅ ህግጋት ባሉበት ይግባኝ መጠየቅ እን ደሚገባቸው እናምናለን፤ ነገር ግን መንግ ስትን ከህጋዊ ካልሆነ ወረራ እና ሁሉንም ሰዎች በአስቸኳይ ሁኔታ የመብትን መጣስ እና በህግጋት ይግባኝ ለመጠየቅ በማይቻል በት ጊዜ ርጋታን ለማግኘት ሁሉም ሰዎች ራሳቸውን፣ ባልንጀሮቻቸውን፣ እና ንብ ረቶቻቸውን በመጠበቅ ጥፋተኞች እንደ ማይሆኑ እናምናለን።

፲፭ ወንጌልን ለምድር ህዝቦች ᐟመስበክ፣ እና በፅድቅ ራሳቸውን ከአለም ክፋት እን ዲያድኑ ማስጠንቀቅ ትክክል እንደሆነ እና ምናለን፤ ነገር ግን በባሪያዎች ላይ ጣልቃ በመግባት፣ ወይም ለእነርሱ የአለቆቻ ቸው ፈቃድ ባለማክበር ወንጌልን መስበክ ወይም ማጥመቅ፣ ወይም ጣልቃ በመግባት ወይም ተጽእኖ በማድረግ በዚህ ህይወት ሁኔታቸው እንዳይደሰቱ ማድረግ፣ በዚ ህም የሰዎችን ህይወት አደጋ ላይ መጣል ትክክለኛ እንደሆነ አናምንም፤ እንደዚህ አይነት ጣልቃ መግባት ህጋዊ ያልሆነ እና ፍትሀዊ እንዳልሆነ እንደሆነ፣ እና በአገ ልጋይነት ሰዎች በግድ እንዲያዙ ለሚፈ ቅደው መንግስት ሰላም አደገኛ እንደሆ ነም እናምናለን።

፲ ᐟ አልማ ፴፡ ፲–፲፩፤ ት. እና ቃ. ፵፪፡ ፹፬–፹፯።

፲ ᐟ ቅ.መ.መ. ውግዘት።

፲፪ ᐟ ቅ.መ.መ. መስበክ፤ የሚስዮን ስራ።

ክፍል ፲፯፤

በሰኔ ፳፯፣ ፲፰፻፳፯ (እ.አ.አ.) በካርቴጅ ኢለኖይ ውስጥ የነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ እና የወንድሙ ፔትሪያርክ ሀይረም ስሚዝ ሰማዕትነትን ይፋ የሆነበት። ይህ መረጃ በ፲፰፻፳፯ (እ.አ.አ.) በትምህርት እና ቃል ኪዳኖች ቅጂ ውስጥ መጨረሻ ላይ ተጨምሮ ነበር፣ ይህም ጆሴፍ እና ሀይረም ስሚዝ በተገደሉበት ጊዜ ለመታ ተም ተዘጋጅቶ ነበር።

፩–፪፣ ጆሴፍ እና ሀይረም በካርቴጅ እስር ቤት ሰማእት ሆኑ፤ ፫፣ የነቢዩ ከሁሉም በላይ የሆነው አቋም ተደነቀ፤ ፬–፯፣ ንጹህ ደማቸው የስራውን እውነትነት እና መለ ኮታዊነት ይመሰክራል።

፩ የዚህን መፅሐፍ እና የመፅሐፈ ሞርሞ ንን ምስክር ለማተም፣ የነቢዩ [ሀ]ጆሴፍ ስሚዝ እና የፔትሪያርክ ሀይረም ስሚዝ [ለ]ሰማዕት ነትን እናሳውቃለን። በሰኔ ፳፯፣ ፲፰፻፳፯ (እ.አ.አ.) ከሰአት በኋላ በአምስት ሰአት፣ ጥቁር የተቀቡ ከ፲፪ እስከ ፪፤ በሆኑ መሳ ሪያ በታጠቀ አመጸኛ ቡድን ሰዎች [ሐ]በካ ርቴጅ እስር ቤት ውስጥ በጥይት ተገደሉ። [መ]ሀይረም ነበር በመጀመሪያ በጥይት የተመ ታው እና በጸጥታም ሲወድቅ፣ *የምትኩኝ ሰው ነኝ!* ብሎ በሀይል ተናገረ። ጆሴፍ ከመ ስኮት ዘለለ፣ እና ይህን ሲሞክርም በጥይት ተመታ፣ *አቤቱ ጌታ አምላኬ!* ብሎ በሀይል ተናገረ። ከሞቱም በኋላ በጥይቶችም ተመ ትተው ነበር፣ እና ሁለቱም በጭካኔ በአራት ጥይቶች ተመትተው ነበር።

፪ በዚያን ጊዜ በክፍሉ ውስጥ የነበሩት ከአስራ ሁለቱት አባላት ሁለቱ፣ [ሀ]ጆን ቴይ ለር እና ዊለርድ ሪቻርድ ብቻ ነበሩ፤ የመጀ መሪያውም በጭካኔ በአራት ጥይቶች ተመ ትቶ ነበር፣ ነገር ግን ከዚህ በኋላም ድኗል፤ የኋለኛው በእግዚአብሔር ጥበቃ በልብሱም ላይ ቀዳዳ ሳይገኝ አመለጠ።

፫ የጌታ [ሀ]ነቢይ እና [ለ]ባለራዕይ ጆሴፍ ስሚዝ፣ ከኢየሱስ በስተቀር፣ በዚህ አለም ውስጥ ለሰዎች ደህንነት ከኖሩ ሌሎች ሰዎች ሁሉ በላይ አድርጎታል። በአጭር በሆነ በሀያ አመት ጊዜ ውስጥ፣ በእግዚአብሔር ስጦታ እና ሀይል የተረጎመውን መፅሐፈ ሞርሞ ንን አምጥቷል፣ እና በሁለት አህጉራት ላይ ይህን ለማተምም ምክንያት ሆኗል፤ ይህም የያዘውን የዘለአለም ወንጌል [ሐ]ሙላ ትን ወደ ምድር አራት ማዕዘናት ልኳል፤ ራዕያት እና ትእዛዛት የተቀናበሩበትን የት ምህርት እና ቃል ኪዳኖች መፅሀፍን፣ እና ሌሎች ብዙ ብልህ መረጃዎችን እና መመ ሪያዎችንም ለሰዎች ልጆች ጥቅም አምጥ ቷል፤ ብዙ ሺህ የኋለኛ ቀን ቅዱሳንን ሰብ ስቧል፣ ታላቅ [መ]ከተማን መስርቷል፣ እና ሊሞት የማይችልን ታዋቂነትን እና ስምን ትቷል። በታላቅነት ኖሯል፣ እና በእግዚአ ብሔር እና በህዝቡ አይኖች ውስጥም በታ ላቅነት ሞቷል፤ እና እንደ ጥንቱም ጊዜ በጌታ እንደተቀቡ ብዙዎችም ተልዕኮውን እና ስራዎቹን [ሠ]በደሙ አስሯል፤ እና ወን ድሙ ሀይረምም ይህንኑ አድርጓል። በህ ይወት አልተለያዩም ነበር፣ እና በሞትም አልተለያዩም!

፬ ጆሴፍ ለህግ ጥያቄ ራሱን አሳልፎ ለመስጠት ወደካርቴጅ ሲሄድ፣ ከመገ ደሉ ሁለት ወይም ሶስት ቀናት በፊት፣ እንዲህ ብሏል፥ “ለመታረድ እንደሚሄድ

፲፯፤ ፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. ስሚዝ፣ ጆሴፍ ዳግማዊ።
ለ ት. እና ቃ. ፭፡፲፭፤ ፮፡፡ ፯፡ ፴።
ቅ.መ.መ. ሰማዕት፣ ሰማዕትነት።
ሐ ቅ.መ.መ. የካርቴጅ እስር ቤት (ዩ.ኤስ.ኤ.)።
መ ቅ.መ.መ. ስሚዝ፣ ሀይረም።
ፀ *ሀ* ቅ.መ.መ. ቴይለር፣ ጆን።
ፐ *ሀ* ቅ.መ.መ. ነቢይ።
ለ ቅ.መ.መ. ባለራዕይ።
ሐ ት. እና ቃ. ፴፭፡ ፲፯፤ ፵፪፡ ፲፪።
ቅ.መ.መ. የወንጌል ዳግም መመለስ።
መ ቅ.መ.መ. ናቩ፣ ኢለኖይ (ዮ.ኤስ.ኤ.)።
ሠ ዕብ. ፱፡ ፲፯–፲፯፤ ት. እና ቃ. ፲፴፯፡ ፴፱።

ᵐበግ እሄዳለሁ፤ ነገር ግን እንደ በጋ ማለዳ የረጋሁ ነኝ፤ እግዚአብሔርን እና ለሁሉም ሰዎች ከማይጎዳ ንጹ ህሊናም አለኝ። በንፅህና እሞታለሁ፣ እና ስለ እኔ ግን እንዲህ ይባላል—ግድያ በታለመበት ተገደለ።”—በዚያም ማለዳ፣ ሀይረም ለመሄድ ከተዘጋጀ በኋላ—ወደ መታረድ ሊባል ይቻላልን? አዎን፣ ነበርና—በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ በኤተር አስራ ሁለተኛ ምዕራፍ መጨረሻ አጠገብ ያለውን የሚቀጥለውን አንቀፅ አነበበ፣ እና ገጹንም አጠፈ፥

፮ እናም እንዲህ ሆነ አህዛብ የጌታ ልግስና ይኖራቸው ዘንድ የመንፈስ ጥንካሬም እንዲያገኙ ወደ ጌታ ፀለዩ። እናም እንዲህ ሆነ ጌታም እንዲህ ሲል ተናገረኝ፥ ልግስና ከሌላቸው አንተ ታማኝ ስለሆንክ ላንተ ምንም አይደለም፤ ስለዚህ፣ ልብስህ ᵐይነ ፃል። እናም ድካምህን በማየትህ በአባቴ ቤት ባዘጋጀሁልህ ስፍራ እንድትቀመጥ ብርቱ ተደርገሀል። እናም አሁን . . . አህዛብን አዎን እናም ደግሞ የምወዳቸው ወንድሞቼን በክርስቶስ ᵃየፍርድ ወንበር ፊት እስካገኛቸው ተሰናበትኳቸው፤ ሰዎችም ሁሉ ልብሶቼ በእናንተ ደም እንዳልተበከሉ ያውቃሉ። ᵇመስካሪዎቼ ሞተዋል፣ እና ምስክራቸውም ተፅዕኖ አለው።

፯ ሀይረም ስሚዝ በሚያዝያ ፤፰፻፱፯ (እ.አ.አ.) አርባ አራት አመቱ ነበር፣ እና ጆሴፍ ስሚዝ በታህሳስ ፤፰፻፱፫ (እ.አ.አ.) ሰላሳ ስምንት አመቱ ነበር፤ እና ከዚህም በኋላ ስሞቻቸው ከሀይማኖት ሰማዕታት ጋር የተመደቡ ሆኑ፤ እና መፅሐፈ ሞርሞንን በሁሉም ሀገሮች ውስጥ የሚያነቡትም፣ እና ይህን የቤተክርስቲያኗ የትምህርት እና ቃል ኪዳኖች መፅሐፍ የተበላሸውን አለም ወደ ደህንነት ለማምጣት በአስራ ዘጠነኛው መቶ አመት ከሁሉም የሚልቅ ደም እንደ ተከፈለበት ያስታውሱ፤ እና እሳት ለእግዚአብሔር ክብር ᵐአረንጓዴን ዛፍ የሚጎዳ ከሆነ፣ የተበላሸውን የወይን ስፍራ ለማፅዳት እንዴት በቀላል የደረቀውን ዛፍ ያነዳል። ለክብር ኖሩ፤ ለክብርም ሞቱ፤ እና ክብርም የዘለአለም ደመወዛቸው ነው። ከዘመን ወደ ዘመን እስከ ትውልድ ድረስ ስሞቻቸው ለተቀደሱት ዕንቁ ይሆናሉ።

፲ ከዚህ በፊት እንዳረጋገጡት፣ በምንም ወንጀል ንጹህ ነበሩ፣ እና በከሀዲዎች እና በክፉ ሰዎች አድማ ብቻ ነበር የታሰሩት፤ እና በካርቴጅ እስር ቤት ወለል ላይ ንጹህ ደማቸው “በሞርሞንነት” ላይ በምድር ፍርድ ቤት ውስጥ ሊወገድ በማይቻል ማህተም የታተመ ነው፣ እና በስቴቱ እስ ተዳዳሪ የተገባው እምነት በመስበር፣ ንጹህ ደማቸውም ለኢለኖይ ስቴት ህጋዊ አልማም ነው፣ አለም ሁሉ ሊከሰው የማይችለው የዘለአለማዊ ወንጌል እውነትነት ምስክርም ነው፤ እና በነጻነት አርማ እና በዩናይትድ ስቴትስ ማግና ካርታ ላይ ንጹህ ደማቸው በሁሉም ሀገሮች መካከል ለሚገኙት የዋህ ሰዎች ለኢየሱስ ክርስቶስ ሀይማኖት አምባሳደር ነው፤ እና ንጹህ ደማቸውም ዮሐንስ ᵐከመሰዊያው በታች ካያቸው ሰማዕታት ንጹህ ደም ጋር ወደ ሰራዊት ጌታ ያን ደም በምድር ላይ እስኪያበቅል ድረስ ይጮሀሉ። አሜን።

ክፍል ፤፱፯፤

በዊንተር ኮርተርስ፣ በእስራኤል ስፍራ፣ በኦማሀ ኔሽን ውስጥ፣ በሚዙሪ ወንዝ ምዕራብ ዳርቻ ላይ፣ በካውንስል ብላፍ አየዋ አጠገብ በፕሬዘደንት ብሪገም ያንግ በኩል የተሰጠ የጌታ ቃል እና ፈቃድ።

፤ ᵃ ኢሳ. ፶፫፡፮።
፪ ᵃ ት. እና ቃ. ፲፯፡፫፡ ፫፤–፫፭።
ᵃ ኤተር ፤፪፡ ፴፮–፴፡
ᵇ ዕብ. ፱፡ ፲፯–፲፯።
፮ ᵃ ሉቃ. ፳፫፡ ፴፭።
፯ ᵃ ራዕ. ፮፡ ፱።

፩–፲፤ የእስራኤል ስፍራ ለምዕራቡ ጉዞ እንዴት እንደሚደራጅ ተገልጿል፤ ፲፫–፳፯፣ ቅዱሳን በብዙዎቹ የወንጌል መሰረቶች እንዲኖሩ ታዘዙ፤ ፳፰–፴፫፣ ቅዱሳን ይዘምሩ፣ እልልታንም ያድርጉ፣ ይጸልዩ፣ እና ጥበብን ይማሩ፤ ፴፬–፴፮፣ ነቢያት የሚገደሉት ይከበሩ እና ጥፋተኞችም ይኮነኑ ዘንድ ነው።

፩ የእስራኤል ስፍራ ለምዕራቡ ጉዞአቸውን የተመልከተ የጌታ ቃል እና ፈቃድ፥

፪ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ [ሀ]ቤተክርስቲያን ህዝብ ሁሉ፣ እና ከእነርሱ ጋር የሚጓዙት በቡድን የጌታ አምላካችንን ትእዛዛት እና ደንብ ለመከተል ቃል ኪዳን እና የተሰፋ ቃል በመግባት ይደራጁ።

፫ ቡድኖችም [ለ]በአንድ መቶዎች አለቃዎች፣ በሀምሳዎች አለቃዎች፣ እና በአስሮች አለቃዎች፣ በሚመሯቸው ፕሬዘደንት እና ሁለት አማካሪዎች፣ በአስራ ሁለት [ሐ]ሐዋርያት አመራር መሰረት ይደራጁ።

፬ እና ይህም [መ]ቃል ኪዳናችን ይሆናል፣ በጌታ [ሠ]ስርዓቶች ሁሉ [ረ]እንሄዳለን።

፭ ሁሉም ቡድኖች የተጣመዱ እንስሣትን፣ ጋሪዎችን፣ የሚያስፈልጓቸውን፣ ልብሶችን፣ እና ሌላ ለጉዞ የሚያስፈልጉትን፣ ቢቻሉም፣ ራሳቸውን ያዘጋጁ።

፮ ቡድኖች ከተደራጁ በኋላ ለሚቀሩት ለመዘጋጀት ለመስራት በሚችሉት ይሂዱ።

፯ እያንዳንዱም ቡድን ከአለቆቻቸውና ከፕሬዘደንቶቻቸው ጋር በሚቀጥለው ጸደይ ምን ያህል ለመሄድ እንደሚችሉ ይወስኑ፤ ከዚያም ብቁ ሰውነት ያላቸው እና ችሎታ ያላቸው ሰዎች የተጠመዱ እንስሣትን፣ ዘሮችን፣ እና የማረሻ እቃዎችን ይዘው የጸደይ አትክልቶችን ለመትከል እንዲሄዱ ፈርቀዳጆች የሚሆኑ ብቁ ቁጥሮችን ምረጡ።

፰ የባልቴት እና አባት የሌላቸው ለቅሶዎች ወደጌታ ጆሮዎች በህዝብ ላይ እንዳ ይመጣ፣ እያንዳድኑም ቡድን በንብረቶቻቸውን በተከፋፈሉበት መጠን፣ [ሠ]ድሆችን፣ [ሀ]ባልቴቶች፣ [ለ]አባቶች የሌላቸውን፣ እና ወደ ጦር ሰራዊነት የሄዱትን ቤተሰቦችን በመውሰድ በእኩል ድርሻን ይሸከሙ።

፱ እያንዳንዱም ቡድን ለዚህ ዘመን ለሚቀሩትም ቤቶች፣ እና እህልን ለመትከልም መሬቶችን ያዘጋጁ፤ እና ይህም ህዝቦቹን በሚመለከት የጌታ ፈቃድ ነው።

፲ እያንዳንዱም ሰው የእራሱን ተፅዕኖ እና ንብረት ይህን ህዝቡ የፅዮንን [መ]ካስማ ጌታ ወደሚወስደው ስፍራ ለመውሰድ ይጠቀም።

፲፩ እና ይህን በንጹህ ልብ፣ በሙሉ ታማኝነት ብታደርጉ፣ [ሠ]ትባረካላችሁ፤ በመንጋዎቻችሁም፣ እና በመሬቶቻችሁ፣ እና በቤቶቻችሁ እና በቤተሰቦቻችሁ ትባረካላችሁ።

፲፪ አገልጋዮቼ ኤዝራ ቲ ቤንሰን እና ኢራስተስ ስኖው ቡድንን ያደራጁ።

፲፫ እና አገልጋዮቼ ኦርሰን ፕራት እና ዊልፈርድ ዉድረፍ ቡድንን ያደራጁ።

፲፬ ደግሞም፣ አገልጋዮቼ አማሳ ላይመን እና ጆርጅ ኤ ስሚዝ ቡድንን ያደራጁ።

፲፭ እና ፕሬዘደንቶችንና የመቶዎችን፣ የሀምሳዎች፣ እና የአስሮች አለቃዎችን ይመድቡ።

፲፮ እና የተመደቡትም ይሂዱ እና ወደ ሰላም ምድርም ለመሄድ ይዘጋጁ ዘንድ ይህን ፈቃዴን ለቅዱሳን ያስተምሩ።

፲፯ ሂዱ እና እንደ ነገርኳችሁም አድርጉ፣ እና ጠላቶቻችሁን አትፍሩ፤ ስራዬን ለማቆም ምንም ሀይል የላቸውምና።

፲፰ ፅዮንም በጊዜዬ [ሠ]ትድናለች።

፲፱ ማንም ሰው እራሱን ከፍ ለማድረግ

፲፱ ፪ [ሀ] ቅ.መ.መ. የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን።
፫ [ሀ] ዘፀአ. ፲፰፡፳–፳፪።
[ለ] ቅ.መ.መ. ሐዋሪያ።
፬ [ሀ] ቅ.መ.መ. ቃል ኪዳን።
[ለ] ቅ.መ.መ. ስነስርዓቶች።
[ሐ] ቅ.መ.መ. መራመድ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መራመድ (መሄድ)።
፰ [ሀ] ቅ.መ.መ. ደሀ።
[ለ] ቅ.መ.መ. ባል የሞተባት።
[ሐ] ያዕ. ፩፡፳፯፣ ፫ ኔፊ ፳፩፡፩።
፲ [ሀ] ቅ.መ.መ. ካስማ።
፲፩ [ሀ] ዘዳግ. ፳፰፡፩–፲፬።
ቅ.መ.መ. መባረክ፣ የተባረከ፣ በረከት።
፲፰ [ሀ] ት. እና ቃ. ፪፡፲፫።

ቢፈልግ እና ᵐምክሬን ባይፈልግ፣ ምንም ሀይል አይኖረውም እና ሞኝነቱም ግልጽ ይደረጋሉ።

፳ ፈልጉ፤ እና የእርስ በርሳችሁን ቃል ኪዳኖች ሁሉ ᵐጠብቁ፤ እና የወንድማች ሁንም ᵃአትመኙ።

፳፩ የእግዚአብሔርን የአምላካችሁን ስም በከንቱ የመጥራትን ክፋት ከራሳችሁ ᵐአስ ወግዱ፤ እኔ ጌታ አምላካችሁ፣ የአባቶቻ ችሁ ᵃአምላክ፣ የአብርሐምና የይስሀቅና የያዕቆብ አምላክ ነኝና።

፳፪ የእስራኤልን ልጆች ከግብፅ ምድር መርቼ ያወጣኋቸው ᵐእኔ ነኝ፤ እና በመጨ ረሻዎቹም ቀናት እጆቼ የእስራኤልን ህዝብ ᵃለማዳን ተዘርግተዋል።

፳፫ እርስ በራስም ᵐመጣላትን አቁሙ፤ እርስ በራስም ᵃክፋት መነጋገርን አቁሙ።

፳፬ ᵐሰካርን አቁሙ፤ እና ቃላቶቻችሁም እርስ በራሳችሁ ᵃየሚያንጹ ይሁኑ።

፳፭ ከባልንጀራችሁ ከተበደራችሁ፣ ᵐየተበረዳችሁን መልሱ፤ እና ለመክፈል ባትችሉም ወዲያው በመሄድ ለባንጀራችሁ ንገሩ፣ አለበለዚያም ይፈርድባችኋልና።

፳፮ ባልንጀሮቻችሁ ᵐያጡትን ነገር ብታ ገኙ፣ ዳግሞም መልሳችሁ እስከምትሰጡም ድረስ በትጋት ፈልጉት።

፳፯ ጥበብ ያለው መጋቢም እንድትሆኑ ዘንድ፣ ያላችሁን ለመጠበቅ ᵐትጉ ሁኑ፤ ይህም የጌታ አምላካችሁ የነጻ ስጦታ ነውና፣ እና እናንተም የእርሱ ᵃመጋቢ ናችሁና።

፳፰ ደስተኛ ብትሆኑ፣ ጌታን ᵐበዝማሬ፣ በሙዚቃ፣ በእልልታ፣ እና በምስጋና ᵃጸሎት እና ᶜበምስጋና አምልኩ።

፳፱ ᵐየከፋችሁ ብትሆኑም፣ ነፍሶቻችሁ ᵃይደሰቱ ዘንድ፣ ጌታ አምላካችሁን በል መና ጥሩ።

፴ ጠላቶቻችሁን አትፍሩ፣ እነርሱ በእ ጆቼ ውስጥ ናቸው እና እንደፈቃዴም አደ ርግባቸዋለሁና።

፴፩ ለእነርሱ ያለኝን ᵐክብር፣ እንዲ ሁም የፅዮንን ክብር፣ ለመቀበል ይዘጋጁ ዘንድ፣ ህዝቤ በሁሉም ነገሮች ᵃመሞከር አለባቸው፤ እና ᶜመገሰፅን ለመቀበል የማ ይችል ለመንግስቴ ብቁ አይደለም።

፴፪ ደንቆሮውም አይኖቹ ይከፈቱ ዘንድ እና እንዲያይ፣ እና ጆሮዎቹም ተከፍ ተው ይሰማ ዘንድ፣ ራሱን ᵐትሁት በማ ድረግ እና ጌታ አምላኩን በመጥራት ᵃጥበ ብን ይማር፤

፴፫ ትሁቱን እና የተዋረደውን አበራላ ቸው እና አምላክ የሌላቸውን እኮንን ዘንድ ᵐመንፈሴን ልኬአለሁና።

፴፬ ወንድሞቻችሁ፣ እንዲሁም ያሰደዷ ችሁ ህዝብ፣ እናንተን እና ምስክሮቻችሁን ᵐአስወግደዋል፤

፴፭ አሁንም በምጥ እንደተያዘች ሴት የሚያሳቅቃቸው ቀን፣ እንዲሁም የሀዘን

፤፤ ᵐ ቅ.መ.መ. ምክር (ስም)።
፳ ᵐ ቅ.መ.መ. ታማኝ፣ ታማኝነት።
ᵃ ቅ.መ.መ. መመኘት።
፳፩ ᵐ ቅ.መ.መ. ማራከስ።
ᵃ ዘፀአ. ፫፡፮፣ ፩ ኔፊ ፲፤፡፲።
፳፪ ᵐ ዘፀአ. ፲፫፡፲፣ ፲፭፣ ኤር. ፪፡፭–፯፣ ፩ ኔፊ ፭፡፲፭፣ አልማ ፴፯፡፴፭፡፡ ቅ.መ.መ. ያህዌህ።
ᵃ ኤር. ፴፡፲፣ ሕዝ. ፭፡፴፣–፴፪፣ ት. እና ቃ. ፴፭፡፴፣ ፴፣–፴።
፳፫ ᵐ ፣ ኔፊ ፲፩፡፳፤–፴ ቅ.መ.መ. ጸብ።
ᵃ ት. እና ቃ. ፳፡፱፡፡ ቅ.መ.መ. ክፉ መናገር።
፳፬ ᵐ ቅ.መ.መ. የጥበብ ቃል።
ᵃ ት. እና ቃ. ፤፳፡፯፡፯።
፳፭ ᵐ መዝ. ፴፯፡፳፤ ፳፩፣ ሞዛያ ፪፡፳፤፡፡ ቅ.መ.መ. ታማኝ፣ ታማኝነት፣ እዳ።
፳፮ ᵐ ዘሌዋ. ፮፡፪፣ ዘዳግ. ፳፪፡፫።
፳፯ ᵐ ቅ.መ.መ. ትጋት።
ᵃ ቅ.መ.መ. መጋቢ፣ መጋቢነት።
፳፰ ᵐ ቅ.መ.መ. መዘመር።
ᵃ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
ᶜ ፪ ዜና ፭፡፲፣ ት. እና ቃ. ፱፤፡፲–፲፮። ቅ.መ.መ. አመስጋኝ፣ ምስጋናን፣ ምስጋና መስጠት።
፳፱ ᵐ ፪ ሳሙ. ፳፪፡፯። ᵃ ቅ.መ.መ. ደስታ።
፴ ᵐ ሮሜ ፰፡፲፣ ት. እና ቃ. ፱፣ ፫–፪። ቅ.መ.መ. ክብር።
ᵃ ት. እና ቃ. ፱፣ ፪። ቅ.መ.መ. ጭንቀት።
ᶜ ቅ.መ.መ. መገሰጽ፣ ተግሳጽ።
፴፩ ᵐ ቅ.መ.መ. ትሁት፣ ትሕትና።
ᵃ ቅ.መ.መ. ጥበብ።
፴፫ ᵐ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
፴፬ ᵐ ቅ.መ.መ. ማሳደድ፣ መሳደድ።

ቀናት፣ ይመጣል፤ እና ወዲያው፣ አዎን፣ በጣም ፈጥነውም፣ ንስሀ ባይገቡ ሀዘናቸ ውም ታላቅ ይሆናል።

፴፤ ነቢያትንና ወደ እነርሱ የተላኩትን ገድለዋልና፤ እና ከምድር በእነርሱ ላይ የሚጮሁትንም ንጹህ ደም አፍሥሠዋል።

፴፭ ስለዚህ፣ በእነዚህ ነገሮች አትደነቁ፣ እናንት ᵐንጹህ አይደላችሁምና፤ ክብሬን ለመቀበል ገና አትችሉም፤ ነገር ግን ከአ ዳም እስከ አብርሐም፣ ከአብርሐም እስከ ሙሴ፣ ከሙሴ እስከ ኢየሱስና ሐዋር ያት፣ እና ከኢየሱስና ሐዋሪያቱ በሚያገለ ግሉኝ አገልጋዮቼ ᵃበመላእክቴ፣ እና ከሰ ማያት በድምጼ ስራዬን እንዲያመጣ በጠ ራሁት፣ እስከ ጆሴፍ ስሚዝ ᵃየሰጠኋቸሁን ቃላቴን ለማክበር ታማኝ ከሆናችሁ፣ ይህ ንንም ታዩታላችሁ፤

፴፮ ይህን መሰረትም መሰረተ፣ እና ታማ ኝም ነበር፤ እና ወደ እኔም ወሰድኩት።

፴፯ ብዙዎች በሞቱ ምክንያት ተደንቀው ነበር፤ ነገር ግን እንዲከብር እና ክፉዎችም ይኮነኑ ዘንድ ᵐምስክሩን ᵃበደሙ ᵃማተሙ አስፈላጊ ነበር።

፴፰ በዚህም የስሜን ምስክር በመተው ብቻ፣ ᵐከጠላቶቻችሁ አላዳንኋችሁም?

፴፱ አሁን፣ ስለዚህ፣ ᵐየቤተክርስቲያኔ ህዝብ ሆይ፣ አድምጡ፤ እና እናንት ᵐሽማ ግሌዎችም አብራችሁ ስሙ፤ ᵃመንግስቴን ተቀብላችኋል።

፴፪ ፍርድ እንዳይመጣባችሁ እና እምነ ታችሁም እንዳይወድቅባችሁ፣ እና ጠላ ቶቻችሁ እንዳያሸንፋችሁ ዘንድ፣ ትእዛ ዛቴን ሁሉ በማክበር ትጉ ሁኑ። በዚህ ጊዜ ተጨማሪ አልገልፅም። አሜን እና አሜን።

ክፍል ፲፯፡

በጥር ፳፭፣ ፲፰፻፲፯ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ በቤተመቅደስ ውስጥ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተሰጠ ራዕይ። ጊዜውም በዚያ ጊዜ ቤተመቅደስን ለመምረቅ በመዘጋ ጀት ስርዓቶችን በሚያስተዳድርበት ጊዜ ነበር።

፩–፪፣ ነቢዩ ወንድሙን አልቭንን በሰ ለስቲያል መንግስት ውስጥ አየ፤ ፫–፱፣ የሙታን ደህንነት ትምህርት ተገለጠ፤ ፲፣ ሁሉም ልጆች በሰለስቲያል መንግስት ውስጥ ይድናሉ።

፩ ᵐሰማያት ተከፈቱልን፣ እና የእግዚአብ ሔርን ᵃሰለስቲያል መንግስትን እና የእዚ ያን ክብር አየሁ፣ ᵃበሰውነት ይሁን ከዚያ ውጪ አላወቅሁም።

፪ በእሳት ᵐነበልባል የተከበበው፣ የዚያ መንግስት ወራሾች የሚገቡበት ᵃበር በጣም ታላቅ ውበት እንዳለውም አየሁ።

፫ ደግሞም ᵐአብና ᵃወልድ የሚቀመጡበ

፴፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. ንጹህ፣ ንጹህነት።
ለ ራዕ. ፲፰፡ ፭፣ ት. እና ቃ. ፲፣ ፲፩–፲፯፣ ፲፰፡ ፲፱፣ ፲፱፡ ፲፱–፳፣ ፳፡ ፳–፳፯፣ ᴶ.ስ.—ታ. ፩፡ ፴–፴፯።
ሐ ሔለ. ፰፡ ፲፰።

፴፱ *ሀ* ሞዛያ ፲፯፡ ፳፣ ት. እና ቃ. ፲፡ ፳፭፡ ፫።
ለ ቅ.መ.መ. ምስክርነት።
ሐ ቅ.መ.መ. ሰማዕት፣ ሰማዕትነት።

፴፪ *ሀ* ዘፀአ. ፳፫፡ ፳፪፣ ት. እና ቃ. ፳፡ ፀ፣ ፲፡ ፲–፲፣ ፲፡ ፲፩።
ለ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን።
ሐ ዳን. ፯፡ ፳፯።

፴፫ *ሀ* የሐዋ. ፯፡ ፶፭–፶፯፣ ፩ ኔፊ ፩፡ ፳፣ ሔለ. ፭፡ ፴፭–፴፱፣ ᴶ.ስ.—ታ. ፩፡ ፴፫።
ለ ቅ.መ.መ. የሰለስቲያል ክብር።
ሐ ፪ ቆሮ. ፲፪፡ ፪–፬፣ ፩ ኔፊ ፲፩፡ ፩፣ ሙሴ ፩፡ ፲፩።

፴፬ *ሀ* ዘፀአ. ፳፬፡ ፲፯፣ ኢሳ. ፴፫፡ ፲ፀ–፲፭፣ ሔለ. ፭፡ ፳፫፣ ት. እና ቃ. ፲፴፡ ፯።
ለ ፪ ኔፊ ፱፡ ፴፭፣ ፴፩፡ ፲፯።

፫ *ሀ* ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ—እግዚአብሔር አብ።
ለ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ—እግዚአብሔር ወልድ።

ትን በጣም ብሩህ የሆነውን የእግዚአብሔር ሐየክብር ዙፋንንም ተመለከትኩ።

፩ ሀበወርቅ ምንጣፍ አምሳል የሆኑትን የመንግስቱን ውብ መንገዶችንም አየሁ።

፪ አባት ሀአዳምን እና ለአብርሐምንም፤ እና ሐአባቴና መእናቴንም፤ ለብዙ ጊዜ ሞቶ የነበረው ወንድሜ መአልቫንንም አየሁ።

፣ እና ጌታ እስራኤልን ሀዳግም ለመሰብሰብ እጁን ከመዘርጋቱ በፊት ከዚህ ህይወት ሄዶ ስለነበረ፣ እና ለኃጢአት ስርየት ለስላልተጠመቀ፣ በዚያ መንግስት ውስጥ እንዴት ሐውርስ እንዳገኘም ተደነቅሁኝ።

፤ እንዲህም ሲል የጌታ ሀድምፅ ወደ እኔ መጣ፥ ለመቆየት ቢፈቀድላቸው ይቀበሉት የነበሩት፣ ይህን ወንጌል ለባለማወቅ የሞቱት ሁሉ የእግዚአብሔር ሐሰለስቲያል መንግስት መወራሾች ይሆናሉ።

፭ ደግሞም በሙሉ ልባቸው ይህን ሀይቀበሉ የነበሩ፣ ካለዚህ እውቀት ከዚህ በኋላ የሞቱት ሁሉ የዚያ መንግስቱ ወራሾች ይሆናሉ፤

፮ እኔ ጌታ ሁሉንም ሰዎች ሀበስራዎቻቸው መሰረት፣ እንደልባቸውም ለምኞት ሐእፈርድባቸዋለሁና።

፯ እና በተጠያቂነት ሀእድሜም ከመድረሳቸው በፊት የሞቱትን ልጆች ሁሉ በሰማይ ሰለስቲያል መንግስት ውስጥ ለእንደዳኑም ተመለከትኩኝ።

ክፍል ፤፱፯፭

በጥቅምት ፫፣ ፲፱፪፲፭ (እ.አ.አ.) በሶልት ሌክ ስቲ፣ ዩታ ውስጥ ለፕሬዘደንት ጆሴፍ ኤፍ ስሚዝ የተሰጠ ራዕይ። በጥቅምት ፩፣ ፲፱፪፲፭ (እ.አ.አ.) በ፹፱ነኛው የቤተክርስቲያኗ የግማሽ አመት አጠቃላይ ጉባኤ መክፈቻ ንግግራቸው ላይ፣ ፕሬዘደንት ስሚዝ ባለፉት ወራት የተለያዩ መለኮታዊ መልእክቶችን እንደተቀበሉ ገለጹ። ፕሬዘደንት ስሚዝ ባለፈው ቀን ከተቀበሏቸው ከእነዚህ አንዱ አዳኝ ሰውነቱ በመቃብር ውስጥ እያለ የሙታንን መንፈስ መጎብኘቱን በሚመለከት ነበር። በጉባኤው መዝጊያ ወዲያውም ተፅፎ ነበር። በጥቅምት ፩፣ ፲፭፲፭ (እ.አ.አ.) ይህም ለቀዳሚ አመራር አማካሪዎች፣ ለአስራ ሑለቱ ቡድን፣ እና ለፔትሪያርክ ቀረበ፣ እና እነርሱም በአንድ ድምፅ ተቀብለውት ነበር።

፩–፣ ፕሬዘደንት ጆሴፍ ኤፍ ስሚዝ ስለ ጴጥሮስ ፅሁፎች እና ጌታ የመንፈስ አለምን ስለመጎብኘቱ ያሰላስሉ ነበር፤ ፤–፭፩፣ ፕሬዘደንት ስሚዝ የሞቱት ጻድ

ፍሐ ኢሳ. ፤፡፡ ፩፣
ሕዝ. ፩፡ ፳፤–፳፫።
፩ ሀ ራዕ. ፳፩፡ ፳፩፣
ት. እና ቃ. ፲፣ ፡፤።
፪ ሀ ቅ.መ.መ. አዳም።
ለ ት. እና ቃ. ፲፱፤ ፡፳፱።
ቅ.መ.መ. አብርሐም።
ሐ ት. እና ቃ. ፲፳፩፡ ፲፱።
ቅ.መ.መ. ስሚዝ፣
ጆሴፍ ቀዳማዊ።
መ ቅ.መ.መ. ስሚዝ፣
ሉሲ ማክ።
ሠ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡ ፩።
፣ ሀ ዮሐ. ፫፡ ፣–፭፣
፤ ኔፊ ፤፡ ፡፫፣
ኤተር ፩፡ ፣፲–፣፤፣
ት. እና ቃ. ፲፯፣ ፣–፣፤፣
፣፣፩፡ ፤፩።
ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣
መጥመቅ።
ለ ቅ.መ.መ. ለሙታን ደህንነት።
ሐ ኢሳ. ፣፩፡ ፣፩፣
፩ ኔፊ ፡፡፤፣ ፣–፣፤፣
ያዕቆ. ፣፡ ፤።
ቅ.መ.መ. እስራኤል—
የእስራኤል መሰብሰብ።
፣ ሀ ሔለ. ፩፡ ፡፣።
ቅ.መ.መ. ራዕይ።
ለ ጆ.ስ.ት. ፩ ጴጥ. ፡፡፡ ፣
(ተጨማሪ)፤
፤ ኔፊ ፤፡ ፡፡፩–፡፡፣
ሞዛያ ፣፩፡ ፡፡፩።
ሐ ቅ.መ.መ. የሰለስቲያል
ክብር።
መ ት. እና ቃ. ፤፤፣ ፣–፤።
፡ ሀ አልማ ፣፡፡ ፡፣፤፣
ት. እና ቃ. ፣፡ ፣፣።
፤ ሀ ቅ.መ.መ. ስራዎች።
ለ ት. እና ቃ. ፡፡፩፡ ፡፣፩።
ቅ.መ.መ. ልብ።
ሐ ራዕ. ፡፡ ፣፤–፣፫።
ቅ.መ.መ. ፍርድ፣
የመጨረሻው።
፣ ሀ ቅ.መ.መ. መልስ
መስጠት፣ ሂሳብ፣
ተጠያቂነት፣ ሀላፊነት።
ለ ቅ.መ.መ. ደህንነት—
የልጆች ደህንነት።

ቃን በገነት ውስጥ ተሰብስበው እና ክርስቶስም በመካከላቸው ያገለገለበትን አዩ፤ ፳፰–፴፯፣ በመናፍስትም መካከል ወንጌልን ለመስበክ እንዴት እንደተደራጀም ተመለከቱ፤ ፴፰–፶፪፣ ከሞት ከመነሳታቸው በፊት የመንፈስ ሁኔታቸውን እንደ ባርነት የሚመለከቱትን አዳምን፣ ሔዋንን፣ እና ብዙ ቅዱሳን ነቢያትን በመንፈስ አለም ውስጥ አዩአቸው፤ ፶፫–፷፣ ዛሬ በፅድቅ የሚሞቱ በመንፈስ አለም ውስጥ አገልግሎታቸውን ይቀጥላሉ።

፩ በጥቅምት ሶስተኛው ቀን፣ በአስራ ዘጠኝ መቶ አስራ ስምንት አመተ ምህረት ውስጥ፣ ቅዱሳን መጻህፍትን በክፍሌ ቁጭ ብዬ [ሀ]አሰላስል ነበር፤

፪ እና ለአለም [ሀ]ቤዛነት፣ የእግዚአብሔር ልጅ ያደረገውን ታላቅ [ለ]የኃጢአት ክፍያ እያሰብኩ ነበር፤

፫ እና [ሀ]የቤዛው ወደአለም መምጣት አብ እና ወልድ ያሳዩትን ታላቅ እና አስደናቂ [ለ]ፍቅርም፤

፬ በእርሱ [ሀ]የኃጢአት ክፍያ፣ እና በወንጌሉ መሰረታዊ መርሆች [ለ]ታዛዥነት፣ የሰው ዘር ይድን ዘንድ እንደ ሆነ አሰላስል ነበር።

፭ በዚህ ተይዤ እያለሁ፣ ከጌታ መሰቀል በኋላ ወንጌሉ ተሰብኮላቸው ለነበሩት [ሀ]በጳንጦስ፣ በገላትያ፣ በቀጰዶቅያም፣ እና በሌሎች የእስያ ክፍሎች ውስጥ ለተበተኑት [ለ]የጥንት ቅዱሳን ሐዋሪያው ጴጥሮስ ወደጻፈው አዕምሮዬ ተመለሰ።

፮ መፅሐፍ ቅዱስን ከፈትኩ እና የጴጥሮስን የመጀመሪያ መልእክት ሶስተኛ እና አራተኛውን ምዕራፎች አነበብኩኝ፣ እና ሳነብም ቀድሞ ከነበሩት በላይ በሚቀጥሉት ምንባቦች በጣም ተነካሁ፥

፯ “ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቶአልና፤ በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ፥

፰ “በእርሱም ደግሞ ሄዶ [ሀ]በወኅኒ ለነበሩ ነፍሳት ሰበከላቸው፤

፱ “ጥቂቶች ማለት ስምንት ነፍስ በውኃ የዳኑበት መርከብ ሲዘጋጅ፥ የእግዚአብሔር ትዕግሥት በኖኅ ዘመን በቈየ ጊዜ ቀድሞ አልታዘዙም።” (፩ ጴጥሮስ ፫፥ ፲፰–፳)።

፲ “እንደሰዎች በሥጋ እንዲፈረድባቸው በመንፈስ ግን እንደ እግዚአብሔር እንዲኖሩ ስለዚህ ምክንያት ወንጌል ለሙታን ደግሞ ተሰብኮላቸው ነበርና።” (፩ ጴጥሮስ ፬፥ ፮)።

፲፩ ስለእነዚህ [ሀ]ስለተጻፉት ነገሮች ሳሰላስል፣ የመረዳት [ለ]አይኖቼ ተከፈቱ፣ እና የጌታ መንፈስ [ሐ]አረፈብኝ፣ እና ታላቁንና ታናሹን [መ]የሙታን ሰራዊትን አየሁ።

፲፪ እና በዚያም በአንድ ስፍራም አብረው የተሰበሰቡ፣ በስጋ ሲኖሩ በኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር [ሀ]ታማኝ የነበሩ፣ ቁጥራቸው ታላቅ የሆኑ [ለ]የጻድቃን የመንፈስ ቡድኖች ነበሩ፤

፲፫ እና እንደ እግዚአብሔር ልጅ አይነት ታላቅ [ሀ]መስዋዕት ያቀረቡ፣ እና በቤዛው ስምም [ለ]ስቃይንም የተቀበሉ ነበሩ።

፲፬ እነዚህ ሁሉ [ሀ]በአብ እግዚአብሔር እና [ለ]በአንድያ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ

፻፴፰ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. ማሰላሰል።
፪ ሀ ቅ.መ.መ. የቤዛነት ዕቅድ።
ለ ማቴ. ፳፥፳፰። ቅ.መ.መ. የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ።
፫ ሀ ቅ.መ.መ. መድኃኒት።
ለ ዮሐ. ፫፥ ፲፮። ቅ.መ.መ. ፍቅር።
፬ ሀ እ.አ. ፩፥ ፫።
ለ ማቴ. ፯፥ ፳፩። ቅ.መ.መ. ታዛዥነት፣ ታዛዥ፣ መታዘዝ።
፭ ሀ ፩ ጴጥ. ፩፥ ፩።
ለ ይህም በፊት የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የነበሩማለት ነው።
፰ ሀ ኢሳ. ፳፩፥ ፩፤ ሉቃ. ፬፥ ፲፰፤ ት. እና ቃ. ፸፮፥ ፸፫–፸፬፤ ፻፳፰፥ ፳፱።
፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. ቅዱሳት መጻህፍት—የቅዱሣት መጻህፍት ዋጋዎች።
ለ ኤፌ. ፩፥ ፲፰፤ ት. እና ቃ. ፸፮፥ ፲፣ ፲፪፣ ፲፱።
ሐ ኢሳ. ፲፩፥ ፪።
መ ቅ.መ.መ. መንፈስ።
፲፪ ሀ ት. እና ቃ. ፮፥ ፲፫፤ ፶፩፥ ፲፱፤ ፸፮፥ ፶፩–፶፫።
ለ ት. እና ቃ. ፸፮፥ ፳፱–፸።
፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. መስዋዕት።
ለ ማቴ. ፭፥ ፲–፲፪።
፲፬ ሀ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ—እግዚአብሔር አብ።
ለ ቅ.መ.መ. አንድያ ልጅ።

ሐጸጋ አማካይነት ለክብሩ መትንሳኤ ፅኑ
መተስፋ ኖሮአቸው ከስጋ ህይወት ተለይ
ተው ነበር።

፲፭ በደስታ እና በተድላ ተሞልተው እን
ደነበሩም አየሁ፣ እና የሚድኑበት ቀን ስለ
መጣ አብረው ተደስተው ነበር።

፲፮ ከሞት በእስራት ቤዛነታቸውን ይገለጽ
ዘንድ የእግዚአብሔር ልጅ ወደ ሰመንፈስ
አለም መምጣትን ተሰብስበው ይጠባበቁ
ነበር።

፲፯ ያንቀላፋውም ትቢያ የሆነው አካላቸው
ወደ ፍጹም ትክክለኛው መልክ፣ በአጥንትም
ከአጥንቱ፣ እና ጅማትና ስጋ በእነርሱም ላይ
ሰበዳግም እንዲመለስ፣ እና ሐመንፈስም ከሰ
ውነት ጋር ደግሞም እንዳይለያዩ፣ መየደስታ
ሙላትን ይቀበሉ ዘንድ ነበር።

፲፰ ብዙዎች ከሞት ሰንሰለት በሚድኑበት
ሰአት እየተደሰቱ፣ እየጠበቁ ሲነጋገሩም፣
የእግዚአብሔር ልጅ ታማኝ ለነበሩት ለታ
ሰሩት ሃጢያትን በማወጅ መጣ፤

፲፱ እና እዛም ዘለአለማዊ ወንጌልን፣
የትንሳኤን እና የሰው ዘር ሰከውድቀትና
ከግል ኃጢአት ሐንስሀ ስለመግባት የቤዛ
ነትን ትምህርት መሰበከላቸው።

፳ ነገር ግን ለክፉዎቹ አልሄደም፣ እና
እግዚአብሔርን በሚጠሉት መካከል እና
በስጋ እያሉ ንስሀ ላልገቡ ራሳቸውን ሰወዳ
በላሹትም ድምጹ አለተነሳም።

፳፩ ወይም የጥንት ነቢያትን ምስክሮች
እና ማስጠንቀቂያዎችን ያስወገዱት አመ
ጸኞችም ፊቱን አላዩትም፣ ወይም ፊቱንም
አልተመለከቱም።

፳፪ እነዚህም በነበሩበት መጭለማ ነገሰ፣
ነገር ግን በጻድቃን መካከል ሰሰላም ነበር፤

፳፫ እና ቅዱሳንም መበቤዛነታቸው ተደ
ሰቱ፣ እናም ሰበጉልበታቸው ተንበርክከው
የእግዚአብሔርን ልጅ እንደቤዛቸው እና
ከሞት እና ከገሀነም ሐሰንሰለት ያዳናቸው
እንደሆነም አምነው ተቀበሉ።

፳፬ መልካቸውም በራ፣ እና የጌታ መድም
ቀትም በእነርሱ ላይ አረፈ፣ እና ለቅዱስ
ስሙም ምስጋናን ሰዘመሩ።

፳፭ አዳኝ በአይሁድና በእስራኤል ቤት
መካከል በአገልግሎቱ፣ ዘለአለማዊ ወንጌ
ልን ሊያስተምራቸው እንደተጋ እና ለንስ
ሀም ለመጥራት ሶስት አመታትን እንዳሳ
ለፈ ስለገባኝ ተደነቅሁኝም፤

፳፮ እና ግን፣ ምንም እንኳን በታላቅ
መሀይል እና ስልጣን ታላቅ ስራዎች፣ እና
ተዕምራትን ቢሰራም እውነትንም ቢያ
ውጅ፣ ከጥቂቶች በስተቀር ድምጹን ያደ
መጡና በመገኘቱም የተደሰቱ፣ እና ከእጆ
ቹም ደህንነትን የተቀበሉ ብዙ አልነበሩም።

፳፯ ነገር ግን ከሞቱት መካከል የነበረው
አገልግሎቱ በተሰቀለበት እና በትንሳኤው
መካከል በነበረው መጥቂት ጊዜ የተወሰነ
ነበር፤

፳፰ ስለጴጥሮስ ቃላትም አሰብኩ—በዚ
ህም ውስጥ እንዲህ አለ የእግዚአብሔር
ልጅ ደግሞ ሄዶ በወኅኒ ለነበሩ ነፍሳት ሰበ

፲፡ሐ ቅ.መ.መ. ጸጋ።
መ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
ሠ ኤተር ፲፪፡፬፣
ሞሮኒ ፯፡፫፣ ፵–፵፩።
ቅ.መ.መ. ተስፋ።
፲፭ ሀ ኢሳ. ፶፭፡፲፭፣
አልማ ፵፡፲፪።
፲፮ ሀ ሞር. ፱፡፲፫።
ለ ሉቃ. ፳፫፡፵፫፣
አልማ ፵፡፲፭–፲፪።
ቅ.መ.መ. ገነት።
፲፯ ሀ ሕዝ. ፴፯፡፩–፲፡
ለ ፪ ኔፊ ፱፡፲–፲፫።
ሐ ት.እና ቃ. ፶፫፡፳–፴፩።
መ ቅ.መ.መ. ደስታ።
፲፰ ሀ ኢሳ. ፰፭፡፩።
ቅ.መ.መ. ለሙታን
ደህንነት።
፲፱ ሀ ቅ.መ.መ. ወንጌል።
ለ ቅ.መ.መ. የአዳም እና
የሔዋን ውድቀት።
ሐ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣
ንስሀ መግባት።
መ ት.እና ቃ. ፴፯፡፴–፴፱።
፳ ሀ አልማ ፵፡፲፫–፲፡
ቅ.መ.መ. ሲያል፤
ክፉ፣ ክፋት።
ለ ፩ ኔፊ ፲፡፳፩።
፳፩ ሀ ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ጭለማ።
ለ ቅ.መ.መ. ሰላም።
፳፫ ሀ ቅ.መ.መ. የቤዛነት ዕቅድ።
ለ ሮሜ ፲፡፡፲፩፣
ሞዛያ ፳፯፡፡ ፴፩።
ሐ ፪ ኔፊ ፩፡፲፫፣
አልማ ፲፪፡፲፩።
፳፬ ሀ መዝ. ፻፡፩–፪፣
ኢሳ. ፳፡፲፱፣
ራዕ. ፳፪፡፭፣
ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፲፯።
ቅ.መ.መ. ብርሀን፣
የክርስቶስ ብርሀን።
ለ ቅ.መ.መ. መዘመር።
፳፯ ሀ ፩ ኔፊ ፲፩፡፳፰።
፳፯ ሀ ማር. ፳፡፴፩።

ከላቸው፤ የእግዚአብሔር ትዕግሥት በኖኅ ዘመን በቂየ ጊዜ ቀድሞ ላልታዘዙትም— እና ከእነርሱ ጋር በነበረው አጭር ጊዜ ለእነ ዚያ መንፈሶች ለመስበክ እና አስፈላጊ የሆ ነውን አገልግሎት ለመፈጸም እንዴት ነበር የቻለው።

፳፩ እና ስለዚህም ሳስብ፣ አይኖቼ ተከ ፈቱ፣ እና ᵐተረዳሁኝም፣ እና በክፉዎች እና ታዛዥ ባልሆኑት እውነትንም በካዱት መካከል እንዲያስተምራቸው ጌታ እንዳ ልሄደም ታየኝ፤

፴ ነገር ግን እነሆ፣ ከጻድቃን መካከል ሀይሎቹን አደራጀ እና ᵐሀይል እና ስልጣ ንን የተላበሱ መልእክተኞቹን መደበ፣ እና እንዲሄዱና የወንጌሉን ብርሀን ᵃበጭለማ ላሉት፣ እንዲሁም ᵃለሁሉም የሰዎች መን ፈሶች እንዲወስዱ ሀላፊነትን ሰጣቸው፤ እና በዚህም ወንጌሉ ለሙታን ተሰብኮ ነበር።

፴፩ እና የተመረጡት መልእክተኞችም ጌታን ᵐየመቀበልን ቀን በማወጅ እና ለታ ሰሩት፣ እንዲሁም ለኃጢአታቸው ንስሀ በመግባት ወንጌሉን ለሚቀበሉት ᵃነጻነትን በመግለጥ ሄዱ።

፴፪ እንደዚህም ነበር በኃጢአታቸው፣ እውነትን ᵐያለማወቅ ወይም በመተላለፍ፣ ነቢያትን አስወግደው ᵃለሞቱት ወንጌሉ የተሰበከው።

፴፫ እነዚህም በእግዚአብሔር ᵐእምነ ትን፣ ለኃጢአት ንስሀ መግባትን፣ ለኃ ጢአት ᵃስርየት ᵇየውክልና ጥምቀትን፣ እጆችን በመጫን የመንፈስ ቅዱስ ᶜስጦ ታን ተምረው ነበር።

፴፬ እና እንደሰዎች በᶜሥጋ ᵐእንዲፈረድ ባቸው በመንፈስ ግን እንደ እግዚአብሔር ይኖሩ ዘንድ ራሳቸውን ብቁ ለማድረግ የሚ ያስፈልጋቸውን የወንጌል መሰረታዊ መር ሆችን ሁሉ ተምረው ነበር።

፴፭ እና ስለዚህ በታናሹና በታላቁ፣ ጻድቅ ባልሆነው እና በታማኙ፣ ቤዛነት በእግዚ አብሔር ልጅ ᵐበመስቀል ላይ ባቀረበው ᵃመስዋዕት በኩል እንደመጣ በሙታኑ መካከል ታወቀ።

፴፮ እንደዚህም አዳኞችን በመንፈስ አለም በቆየበት ጊዜ በስጋቸው ስለእርሱ የመሰከሩትን ታማኝ ᵐነቢያት መናፍስትን በማስተማር እና በማዘጋጀት ጊዜውን አን ዳሳለፈ ታውቋል፤

፴፯ ᵐበአመጻቸው እና በመተላለፋቸው ምክንያት ራሱ በግል ሊሄድላቸው ለማ ይችለው፣ እነርሱም በአገልጋዮቹ አገልግ ሎት በኩል ቃላቶቹን ይሰሙ ዘንድ፣ የቤዛ ነት መልእክትን ለሙታን ሁሉ እንዲወስዱ ታውቋል።

፴፰ በዚህ ታላቅ የጻድቃን ስብሰባ ከተሰ በሰቡት ታላቅ እና ሀያል ከሆኑት መካከል በዘመናት የሸመገለውና የሁሉም አባት፣ አባት ᵐአዳም ነበር፣

፴፱ እና የክብርም እናት ᵐሔዋን፣ በዘመ ናት ውስጥ የኖሩት እና እውነት እና ህያው እግዚአብሔርን ካመለኩ ከብዙዎቹ ታማኝ ሴት ልጆቿ ጋር።

፴ የመጀመሪያው ᵐሰማዕት ᵃአቤል እና አባቱን አዳምን ᵃየሚመስለው ከሀይለኞቹ አንዱ ወንድሙ ᵐሴትም በዚያ ነበሩ።

፴፱ ᵐ ት. እና ቃ. ᎾᎾ፡ ᎾᎿᎿ።
፴ ᵐ ሉቃ. ᎾᎾ፡ ᎾᎿᎿ።
ᵃ ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ጭለማ።
ᵇ ት. እና ቃ. ᎾᎾ፡ ᎾᎿᎿ።
፴፩ ᵐ ኢሳ. ᎾᎾ፡ ᎾᎿᎿ፤
ሉቃ. ᎾᎾ፡ ᎾᎿᎿ–ᎾᎿᎿ።
ᵃ ቅ.መ.መ. መብት።
፴፪ ᵐ ት. እና ቃ. ᎾᎾᎾ፡ ᎾᎿᎿ።
ᵃ ቅ.መ.መ. እውቀት።
ᵇ ዮሐ. ᎾᎾ፡ ᎾᎿᎿ–ᎾᎿᎿ።
፴፫ ᵐ ኢ.ኢ. ᎾᎾ፡ ᎾᎿᎿ።
ᵃ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
ᵇ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ስርየት።
ᶜ ቅ.መ.መ. ስነስርዓቶች— የወኪል ስነስርዓት፣ ጥምቀት፣ መጥመቅ— ለሙታን መጠመቅ።
ᵈ ቅ.መ.መ. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ።
፴፬ ᵐ ቅ.መ.መ. ፍርድ፣ የመጨረሻው።
ᶜ ᵐ ቅ.መ.መ. መስቀል፤ መስቀል።
ᵃ አልማ ᎾᎾ፡ ᎾᎿᎿ–ᎾᎿᎿ።
ᵃ ቅ.መ.መ. መስዋዕት፤ የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ።
፴፭ ᵐ ት. እና ቃ. ᎾᎾᎾ፡ ᎾᎿᎿ።
ᵃ ᵐ ት. እና ቃ. ᎾᎾᎾ፡ ᎾᎾ።
ᵃ ቅ.መ.መ. አመጽ።
፴፮ ᵐ ቅ.መ.መ. አዳም።
፴፯ ᵐ ሙሴ ᎾᎾ፡ ᎾᎾᎿᎿ።
ᵃ ቅ.መ.መ. ሔዋን።
ᵐ ᵐ ቅ.መ.መ. ሰማዕት፣ ሰማዕትነት።
ᵃ ቅ.መ.መ. አቤል።
ᵇ ዘፍጥ. ᎾᎾ፡ ᎾᎿ፤ ሙሴ ᎾᎾ፡ ᎾᎿ።
ᶜ ቅ.መ.መ. ሴት።

፵፩ ስለጎርፉ ማስጠንቀቂያ የሰጠው [ሀ]ኖኅ፣ ታላቁ [ለ]ሊቀ ካህን [ሐ]ሴም፤ የታማኞቹ አባት [መ]አብርሐም፤ [ሠ]ይስሀቅ፣ [ረ]ያዕቆብ፣ እና የእስራኤል ታላቅ ህግ ሰጪ [ሰ]ሙሴ፤

፵፪ እና በትንቢትም አዳኙ ልባቸው የተሰበረውን ይጠግን ዘንድ፣ [ሀ]ለተማረኩትም ነጻነትን [ለ]ለታሰሩትም መፈታትን ይናገር ዘንድ ተቀብቷል ያለው [ሐ]ኢሳይያስም በዚያ ነበሩ።

፵፫ በተጨማሪም፣ በራዕይ እንደ ህያው ነፍሳት ሙታን [ሀ]በትንሳኤ እንደገና ሲመጡ ወደፊትም በስጋ የሚሸፈኑትን [ለ]የደረቁ አጥንቶች የተሞሉበት ታላቅ ሸለቆ ያየው [ሐ]ሕዝቅኤል፤

፵፬ ደግሞም የማይጠፋው ወይም ለሌሎች ሰዎች የማይሰጠው የእግዚአብሔር [ሀ]መንግስት በኋለኞቹ ቀናት መመስረትን ቀድሞ አይቶ እና ቀድሞ ነግሮ የነበረው [ለ]ዳንኤልም፤

፵፭ ከሙሴ ጋር [ሀ]በክብር የመለወጥ ተራራ ላይ የነበረው [ለ]ኢልያ፤

፵፮ እና [ሀ]ስለኤልያስ መምጣት የመሰከረው ነቢዩ [ለ]ሚልክያስ—ስለዚህም ሞሮኒ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝና የሚያስፈራው [ሐ]የጌታ ቀን ከመምጣቱ በፊት ይመጣል በማለት ያወጀው ሞሮኒም—በዚያ ነበሩ።

፵፯ ነቢዩ ኤልያስ በልጆች [ሀ]ልብ ውስጥ የአባቶቻቸውን ቃል ኪዳኖች ይተክላል፣

፵፰ ለሙታን ቤዛነት፣ እና ልጆችን ከወላጆቻቸው ጋር [ሀ]ለማስተሳሰር፣ መላው ምድር በምጽአቱ እንዳይረገሙ እና እንዳይጠፉ ዘንድ፣ [ለ]በዘመን ፍጻሜ በጌታ [ሐ]ቤተመቅደሶች ውስጥ የሚደረገውን ታላቅ [መ]ስራ ቀድሞ ለማሳየት።

፵፱ እነዚህ ሁሉ እና ብዙ ተጨማሪዎች፣ እንዲሁም በኔፉውያን መካከል የኖሩት እና ስለእግዚአብሔር ልጅ መምጣት የመሰከሩት [ሀ]ነቢያት፣ በታላቁ ስብሰባ ውስጥ በመደባለቅ እና ደህንነታቸውን ለመጠበቅ፣

፶ ሙታን ሰውነታቸው [ሀ]ከመንፈሳቸው ለረዥም ጊዜ መለየቱን እንደ [ለ]ባርነት ተመልክተውታልና።

፶፩ እነዚህንም ጌታ አስተማረ፣ እና ከትንሳኤው በኋላ ወደ አባቱ መንግስት በመግባት፣ [ሀ]በህያውነት እና [ለ]በዘለአለም ህይወት አክሊል ይጫንላቸው ዘንድም እንዲመጡ [ሐ]ሀይልን ሰጣቸው፣

፶፪ እና ከዚህም በኋላ በጌታ ቃል እንደተገባው በአገልግሎታቸው እንዲቀጥሉ፣ እና ለሚወዱትም ተጠብቀው የነበሩትን [ሀ]በረከቶች ሁሉ ተካፋይ እንዲሆኑ።

፶፫ ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ፣ እና አባቴ ሀይረም ስሚዝ፣ ብሪገም ያንግ፣ ጆን ቴይለር፣ ዊልፈርድ ዉድረፍ፣ እና በዘመን ሙላት በታላቁ የኋለኛ ቀን ስራዎች [ሀ]መሰረትን

፵፩ ሀ ቅ.መ.መ. ኖኅ፣ የመፅሐፍ ቅዱስ የአባቶች አለቃ።
ለ ቅ.መ.መ. ሊቀ ካህን።
ሐ ቅ.መ.መ. ሴም።
መ ዘፍጥ. ፲፯፥፩–፰። ቅ.መ.መ. አብርሐም።
ሠ ዘፍጥ. ፳፩፥፩–፭። ቅ.መ.መ. ይስሐቅ።
ረ ዘፍጥ. ፴፭፥፱–፲፭። ቅ.መ.መ. ያዕቆብ፣ የይስሐቅ ልጅ።
ሰ ቅ.መ.መ. ሙሴ።
፵፪ ሀ ኢሳ. ፷፩፥፩–፪።
ለ ቅ.መ.መ. ሲዖል።
ሐ ቅ.መ.መ. ኢሳይያስ።
፵፫ ሀ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
ለ ሕዝ. ፴፯፥፩–፲፬።
ሐ ቅ.መ.መ. ሕዝቅኤል።
፵፬ ሀ ዳን. ፪፥፵፬–፵፭። ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር መንግስት ወይም መንግስተ ሰማያት።
ለ ቅ.መ.መ. ዳንኤል።
፵፭ ሀ ቅ.መ.መ. መለወጥ።
ለ ቅ.መ.መ. ኢልያ።
፵፮ ሀ ት. እና ቃ. ፻፲፥፲፫–፲፭። ቅ.መ.መ. ኤልያስ።
ለ ሚል. ፬፥፭–፮፤ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፴፮–፴፱። ቅ.መ.መ. ሚልክያስ።
ሐ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
፵፯ ሀ ት. እና ቃ. ፻፳፰፥፲፯።
፵፰ ሀ ቅ.መ.መ. ማተም፣ ማስተሳሰር፤ ቤተሰብ—ዘለአለማዊ ቤተሰብ።
ለ ቅ.መ.መ. ዘመን።
ሐ ቅ.መ.መ. ቤተመቅደስ፣ የጌታ ቤት።
መ ቅ.መ.መ. ለሙታን ደህንነት።
፵፱ ሀ ሔለ. ፰፥፲፱–፳፪።
፶ ሀ ቅ.መ.መ. መንፈስ።
ለ ት. እና ቃ. ፵፭፥፲፯።
፶፩ ሀ ቅ.መ.መ. የማይሞት፣ አለሟችነት።
ለ ት. እና ቃ. ፳፱፥፵፫። ቅ.መ.መ. የዘለዓለም ህይወት።
ሐ ፩ ቆሮ. ፮፥፲፬፤ አልማ ፵፥፲፱–፳፩።
፶፪ ሀ ኢሳ. ፷፬፥፬፤ ፩ ቆሮ. ፪፥፱፤ ት. እና ቃ. ፲፬፥፯።
፶፫ ሀ ት. እና ቃ. ፷፬፥፴፫።

ለመመስረት እንዲመጡ ^የጠበቁት ሌሎች ምርጥ መናፍስት፣

፶፩ በተጨማሪም ቤተመቅደሶችን ለመገንባት እና በእነዚያም ውስጥ *ለሙታን ቤዛነት ስነስርዓቶችን ለማከናወን የጠበቁት ምርጥ መናፍስትም በመንፈስ አለም ውስጥ ነበሩ።

፶፪ እነርሱም በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ውስጥ መሪዎች እንዲሆኑ *የተመረጡት ^በተከበሩትና በታላቁ መካከል እንደነበሩም አየሁ።

፶፫ ከመወለዳቸውም በፊት ከብዙ ሌሎች ጋር የመጀመሪያ ትምህርታቸውን በመንፈስ አለም ውስጥ የተቀበሉት እና በጌታ *ጊዜ ^በወይን ስፍራው ለሰዎች የነፍስ ደህንነት እንዲያገለግሉ ለመምጣት ^ተዘጋጅተውም ነበር።

፶፬ የዚህ ዘመን ታማኝ *ሽማግሌዎችም ከዚህ ህይወት ሲሄዱ የንስሀ መግባት እና በእግዚአብሔር አንድያ ልጅ መስዋዕት በኩል የቤዛነት ወንጌልን ^በጭለማ ውስጥ እና በሙታን መንፈሶች ታላቅ አለማት ውስጥ በኃጢአት ባርነት ላሉት በመስበክ አገልግሎታቸውን እንደሚቀጥሉ አየሁ።

፶፭ ንስሀ የገቡ ሙታንም የእግዚአብሔር ቤት *ስርዓቶችን በማክበር ^ይድናሉ፣

፶፮ እና የተላለፉት ቅጣታቸውን ከተቀበሉና *ለመንጻትም ከታጠቡ በኋላ፣ ^በስራዎቻቸው መሰረት ደመወዛቸውን ይቀበላሉ፣ የደህንነት ወራሾች ናቸውና።

፶፯ እንደዚህም ነበር የሙታን ቤዛነት የተገለጠልኝ፣ እና እመሰክራለሁም፣ እና በጌታ እና አዳኝ በሆነው፣ እንዲሁም በኢየሱስ ክርስቶስ፣ በረከት በኩል ይህ መዝገብ *እውነት እንደሆነ አውቃለሁ፣ እንዲህም ይሁን። አሜን።

፶፫ ለ ቅ.መ.መ. ቀድሞ መመረጥ።
፶፩ ሀ ቅ.መ.መ. ስነስርዓቶች—የወኪል ስነስርዓት።
፶፭ ሀ ቅ.መ.መ. ቀድሞ መመረጥ።
ለ አብር. ፫፡ ፳፪–፳፩።
፶፮ ሀ የሐዋ. ፲፯፡ ፳፬–፳፯።
ለ ያዕቆ. ፮፡ ፪–፫።
ቅ.መ.መ. የጌታ የወይን አትክልት ስፍራ።
ሐ ኢዮብ ፴፯፡ ፬–፯፣ አልማ ፲፫፡ ፫–፯።
፶፯ ሀ ቅ.መ.መ. ሽማግሌ።
ለ ቅ.መ.መ. ሲያል።
፶፰ ሀ ቅ.መ.መ. ስነስርዓቶች።
ለ ቅ.መ.መ. ቤዛ፣ ማዳን፣ ቤዛነት።
፶፱ ሀ አልማ ፭፡ ፲፯–፳፪።
ቅ.መ.መ. ይቅርታ ማድረግ።
ለ ቅ.መ.መ. ስራዎች።
፷ ሀ ቅ.መ.መ. እውነት።

አስተዳደሪያዊ አዋጅ ፩

መፅሐፍ ቅዱስ እና መፅሐፈ ሞርሞን እንደሚያስተምሩት፣ እርሱ ካላወጀበት በስተቀር አንድ ሚስት ብቻ ማግባት የእግዚአብሔር መሰረታዊ መርሆ እንደሆነ ያስተምራሉ (፪ ሳሙኤል ፲፪፡ ፣ ፯–፰ እና ያዕቆብ ፪፡ ፳፯፣ ፴ ተመልከቱ)። ለጆሴፍ ስሚዝ ከተሰጠ ረዕይ በኋላ፣ የብዛት ሚስቶች ማግባት ልምድ በቤተክርስቲያኗ በ፲፰፻፴ (እ.አ.አ.) አመታት መጀመሪያ ላይ ተመስርቶ ነበር (ክፍል ፴፴፪ን ተመልከቱ)። ከ፲፰፻፴ እስከ ፲፰፻፹ (እ.አ.አ.) አመታት፣ የዩናይትድ ስቴትስ መንግስት ይህን የሀይማኖት ልምድ ህገ ወጥ የሚያደርጉ ህግጋትን መሰረተ። በመጨረሻም ህግጋቱ ትክክለኛ እንደሆኑ የዩ.ኤስ. ከፍተኛ ፍርድ ቤት አረጋገጠ። ራዕይን ከተቀበሉ በኋላ፣ ፕሬዘደንት ዊልፈርድ ዉድረፍ የሚቀጥለውን መግለጫ ሰጡ፣ ይህም በቤተክርስቲያኗ እንደ ስልጣንና እንደሚያስተሳስር በጥቅምት ፯፣ ፲፰፻፹ (እ.አ.አ.) ተቀባይነትን አገኘ። ይህም ለቤተክርስቲያኗ የብዛት ሚስቶች የማግባት ልምድ መጨረሻ ሆነ።

ለሚመለከተው ሁሉ፥

የዩታ ኮሚሲዮን በቅርቡ በአገር ውስጥ ጸሀፊ መግለጫ ውስጥ የብዙ ጋብቻ ስርዓቶች እንደሚፈጸሙ እና ባለፈው ሰኔ ወይም ባለፈው አመት አርባ ተመሳሳይ ጋብቻዎች በዩታ ውስጥ እንደተደረጉ፣ ደግሞም በህዝባዊ ንግግሮች የቤተክርስቲያኗ መሪዎች ካንድ ሚስት በላይ የማግባት ልምድ እንዲቀጥል አስተምረዋል፣ አበረታትተዋል፣ እና ገፋፍተዋል የሚል ለፖለቲካ አላማዎች በብዛት የታተሙ ወረቀቶች ከሶልት ሌክ ስቲ ተልከው ነበር—

እኔ፣ ስለዚህ፣ እንደ ኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ፕሬዘ ደንት በአፅኖት፣ እነዚህ ክሶች ሀሰት እንደሆኑ እገልጻለሁ። ከአንድ ሚስት በላይ ማግ ባትን ወይም ጋብቻን ማብዛትን እያስተማርን ወይም ማንም ሰው ወደዚህ ልምድ እን ዲገባም እየፈቀድን አይደለም፣ እና አርባ ወይም ማንኛቸውም የብዙ የጋብቻ ስርዓቶች በዚህ ጊዜ በቤተመቅደሳችን ውስጥ ወይም በግዛቱ ማንኛውም ስፍራ እየተከናወነ እንዳ ልሆነም እመሰክራለሁ።

በጸደይ ፲፰፻፹፱ (እ.አ.አ.) በሶልት ሌክ ስቲ መንፈሳዊ ስጦታ ቤት ውስጥ ጋብቻ እን ደተፈጸመ የሚባልበት አንድ ጉዳይ ተመዝግቦ ነበር፣ ነገር ግን ያንን ስነ ስርዓት ማን እን ደፈጸመው ለማወቅ አልቻልኩም፤ በዚህ ጉዳይ ላይ የተደረገው ምንም ነገር እኔ በማላ ውቅበት ነበር። በመንፈሳዊ ስጦታ ቤት ውስጥ ተደረገ ስለተባለውም ያለመዘግየት በእኔ ትእዛዜ ፈርሷል።

እነዚህም ህግጋት በመጨረሻው አማራጭ ፍርድ ቤት ህገ መንግስታዊ እንደሆነ የፈ ረዱበት፣ ብዙ ሚስቶችን ስለማግባት ኮንግረሥ ባሳለፋቸው ህግጋት መሰረት፣ እነዚህን ህግጋት ለማክበርና በምመራቸው ከቤተክርስቲያኗ አባላት ጋር ያለኝን ተፅዕኖ በመጠቀም እንደእኔ እንዲያደርጉ ለማድረግ ያለኝን ፈቃድ በዚህ እገልጻለሁ።

በተጠቀሰው ጊዜ በቤተክርስቲያኗ እኔ ወይም አብሬአቸው ከምሰራው በምናስተም ራቸው ውስጥ ብዙ ሚስቶችን ማግባትን የሚያበረታታ ወይም እንደሚያዳብር ሊተረጎም የሚችል ምንም የለም፤ እና የቤተክርስቲያኗ ማንም ሽማግሌ እንደዚህ አይነት ትምህር ትን እንደሚሰጥ የሚመስል ቋንቋዎችን በተጠቀመ ጊዜ፣ ወዲያው ተገሰጿል። አሁንም ለኋለኛው ቀን ቅዱሳን ምክሬ በምድር ህግ የተወገደውን ምንም ጋብቻ ውል ማስገባትን እንዲያቆሙ እንደሆነ በህዝብ ዘንድ አውጃለሁ።

ዊልፈርድ ዉድረፍ
የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ
ቤተክርስቲያን ፕሬዘደንት።

ፕሬዘደንት ሎሬንዞ ስኖው የሚቀጥሉትን አቀረቡ፥

“ዊልፈርድ ዉድረፍን እንደ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ፕሬዘደንት፣ እና በዚህ ጊዜ የማተም ስነስርዓቶችን ቁልፎች በምድር ላይ እንደያዘ ሰው በመቀበል፣ በመስከረም ፳፬ ቀን ፲፰፻፹ (እ.አ.አ.) ቀን እንድንሰማው የተነበበውን ህዝባዊ መግለጫን ለመስጠት ሙሉ ስልጣን እንዳላቸው በመቀበል፣ በአጠቃላይ ጉባኤ እንደተ ሰበሰብነው ቤተክርስትያን ይህን ብዙ ሚስቶች ማግባትን በሚመለከት ያወጁት አስገዳጅ እና በስልጣን እንደሆነም እንቀበላለን።”

ሶልት ሌክ ስቲ፣ ዩታ፣ ጥቅምት ፲፣ ፲፰፻፹ (እ.አ.አ.)።

ከፕሬዘደንት ዊልፈርድ ዉድረፍ
ስለህዝባዊ መግለጫ ከሰጡት
ሶስት ንግግሮች የተወሰደ ምንባብ

ጌታ እኔን ወይም በዚህች ቤተክርስቲያን እንደ ፕሬዘደንት የሚቆም ማንንም ሰው እናንተን ወደ ስህተት እንዲመራ አይፈቅድም። ይህም በአላማው ውስጥ አይደለም። ይህም በእግዚአብሔር ልብ አይደለም። ይህን ብሞክር፣ ጌታ ከስፍራዬ ያስወጣኛል፣ እና የሰዎች ልጆችን ከእግዚአብሔር ቃላት እና ከሀላፊነታቸው እንዲሳሳቱ የሚጥረውንም እንዲሁ ያደርጋል። (የቤተክርስቲያኗ ሰላሳ አንደኛው የአጠቃላይ ጉባኤ፣ ጥቅምት ፮ ቀን ፲፰፻፶ [እ.አ.አ.]፣ ሶልት ሌክ ስቲ፣ ዩታ። በ*Deseret Evening News* [ደዘረት የምሽት ኮኮብ ዜና] ሀተታ፣ ጥቅምት ፲፩ ቀን ፲፰፻፶፣ ገፅ ፪።)

ማንም ይኑር ወይም ይሙት፣ ወይም ማንም ይህችን ቤተክርስቲያን ለመምራት መጠራቱ አስፈላጊ አይደለም፣ በሁሉም ገዢ እግዚአብሔር መነሳሳት መምራት አለባቸው። ይህን በዚህ መንገድ ባያደርጉ፣ ሊያደርጉትም አይችሉም. . .።

አንዳንድ፣ እና በጣም አስፈላጊ የሆኑትንም፣ ራዕዮችን ባለፉት ጊዜያት አግኝቻለሁ፣ እና ጌታ ምን እንዳለኝም እነግራችኋለሁ። ህዝባዊ መግለጫ ስለተባለው ታስቡበት ዘንድ ላድርግ. . .።

ጌታ የኋለኛውን ቀን ቅዱሳንን ጥያቄ እንድጠይቅ ነገረኝ፣ እና የምላቸውን ቢሰሙና የምጠይቃቸውንም ቢመልሱ፣ በእግዚአብሔር መንፈስ እና ሀይል ሁሉም እንደ አንድ ይመልሳሉ፣ እና ስለዚህ ጉዳይም በአንድነት ያምናሉ በማለትም ነገረኝ።

ጥያቄውም ይህ ነው፥ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን መከታተል ያለባቸው የጥበብ መንገድ የትኛው ነው—የቤተመቅደሶችን ሁሉ ማጣትን እና መወረስን፣ እና በእነርሱም ውስጥ ለሀያው እና ለሙታን የሚደረጉትን ስርዓቶችን ማቆምን፣ እና የቤተክርስቲያኗ ቀዳሚ አመራርና አስራ ሑለት፣ እና የቤተሰብ መሪዎች መታሰርን፣ እና የህዝብ (ይህን ልምድ የሚያቆሙትን ሁሉ) የግለሰብ ንብረቶች መወሰድን ክፍያ በማድረግ የሀገር ህግጋትና ስልሳ ሚልዮን የሚቃወሙትን ብዙ ሚስት የማግባት ልምድን ለመቀጠል መሞከርን፤ ወይም ይህን መሰረታዊ መርሆ በማክበር ከደረሰብን እና ከተሰቃየናቸው በኋላ፣ በህጉ ታዛዥ በመሆን እና ይህን ልምድ በማቆም፣ እና ይህን በማድረግም ነቢያትን፣ ሐዋርያትን፣ እና አባቶችን ህዝብን እንዲያስተምሩ እና የቤተክርስቲያኗን ሀላፊነታቸውን እንዲያከናውኑ በቤት በማቆየት፣ እና ደግሞም የወንጌልን ስርዓቶችን ለህያው እና ለሙታን ለማድረግ እንዲችሉ ቤተመቅደሶችን በቅዱሳን እጆች ውስጥ እንዲቀሩ በማድረግ ነውን?

ጌታ በመግለጫ እና በራዕይ ይህን ልምድ ባናቆም ምን እንደሚደርስ አሳይቶኛል። ይህንን ካላቆምን፣ ማና ችሁም በዚህ በሎጋን ቤተመቅደስ ላሉት ለማንኛውም ሰው ምንም ጥቅም ባልሰጣችሁ ነበር፤ በፅዮን ምድር ውስጥ ሁሉም ስነ ስርዓቶች በቆሙ ነበር። በእስራኤልም ግራ መግባት በነገሰ ነበር፣ እና ብዙ ሰዎችም እስረኞች በሆኑ ነበር። ይህም ችግር በቤተክርስቲያኗ ሙላት ላይ ይመጣ ነበር፣ እና ይህን ልምድ ለማቆምም እንገደድ ነበር። አሁን፣ ጥያቄውም በዚህ መንገድ ይቁም፣ ወይስ ጌታ በገለጸልን መንገድ፣ እና ነብያቶቻችንን እና ሐዋሪያቶቻችንን እና አባቶችን በነጻነት እንተዋቸው እና ሙታን እንዲድኑም ቤተመቅደሳችንን በህዝብ እጆች ውስጥ እንተዋቸው ነው። በዚህ ህዝብ አማካይነት በመንፈስ አለም ውስጥ ካለው የእስር ቤት ታላቅ ቁጥር ያላቸው ድነዋል፣ እና ስራው ይቀጥል ወይስ ይቁም? ይህን ጥያቄ በኋለኛው ቀን ቅዱሳን ፊት አስቀምጣለሁ። ለራሳችሁ መፍረድ አለባችሁ። ለራሳችሁ እንድትመልሱበት እፈልጋችኋለሁ። እኔ አልመልሰውም፤ ነገር ግን የወሰድነውን መንገድ ባንወስድ ኖሮ ይህም እንደ ህዝብ ልንገኝበት የምንችልበት ሁኔታ ነው እላችኋለሁ።

. . .አንድ ነገር ባይደረግ ኖሮ ምን ሊሆን እንደሚችልም አይቼ ነበር። ይህም መንፈስ በእኔ ላይ ለረዥም ጊዜ ኖሮኝም ነበር። ነገር ግን ይህን ለማለት እፈልጋለሁ፥ የእግዚአብሔር ሰማይ ያደረግሁትን እንዳደርግ ባያዘኝ ኖሮ፣ ቤተመቅደሶችን ሁሉ ከእጆቻችን አስወጣ ነበር፤ ራሴም ወደ እስር ቤት፣ እና እያንዳንዱንም ሰው ወደዚያ እንዲሄድ አደርግ ነበር፤ እና ያን እንዳደርግ የታዘዝኩበት ሰዓት ሲመጣ፣ ይህም ለእኔ ግልፅ ነበር። ከጌታም ፊት ሄድኩ፣ እና ጌታ እንድፅፍ የነገረኝን ጻፍኩ. . .።

ይህን ከእናንተው ዘንድ የምተወው እናንት እንድታሰላስሉበት እና እንድታስቡበት ነው። ጌታ ከእኛ ጋር እየሰራ ነው። [ካሽ ካስማ ጉባኤ፣ ሎገን፣ ዩታ፣ እሁድ፣ ህዳር ፩ ቀን ፲፰፻፶፩ (እ.አ.አ.)። በ*Deseret Weekly* [የደዘረት ሳምንታዊ ዜና] ሀተታ ውስጥ፣ ህዳር ፲፱ ቀን ፲፰፻፶፩ (እ.አ.አ.)።]

አሁን የተገለጸልኝን እና በዚህ ነገር የእግዚአብሔር ልጅ ምን እንደፈጸመ እነግራችኋለሁ. . .። ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር ህያው እንደሆነ፣ ህዝባዊ መግለጫው ባይሰጥ ኖሮ እነዚህ ነገሮች ሁሉ በሆኑ ነበር። ስለ ዚህ፣ በአዕምሮው ውስጥ ላሉት አላማዎች የእግዚአብሔር ልጅ ያንን ነገር ለቤተክርስቲያኗ እና ለአለም እንዲቀርቡ ፈቃዱ ነበር። ጌታ የፅዮንን መመስረት አውጇል። የዚህ ቤተመቅደስ መፈጸምን አውጇል። የህያው እና የሙታን ደህንነት በእነዚህ ተራሮች ሸለቆዎችም ውስጥ መሰጠት እንዳለባቸውም አውጇል። እና ሁሉን

የሚገዛ እግዚአብሔር ያወጀውን ዲያብሎስ ሊያሰናክል አይችልም። ያንን ለመረዳት ከቻላችሁ፣ ያም ለዚህ ቁልፍ ነው። (በሚያዝያ ፲፯፻፶ [እ.አ.አ.] በሶልት ሌክ ቤተመቅደስ መመረቂያ ስድስተኛ ስብሰባ ላይ ከተሰጠው ንግግር። የመመረቂያው ስብሰባ የተተነበየበት ፅሑፍ፣ ፅሑፋዊ ሰነዶች፣ የቤተክርስቲያን ታሪክ ዲፓርትመንት፣ ሶልት ሌክ ስቲ፣ ዩታ።)

አስተዳደሪያዊ አዋጅ ፪

መፅሐፈ ሞርሞን እንደሚገልጸው፣ "ሁሉም ለእግዚአብሔር አንድ ናቸው፣" እንዲሁም "ጥቁርም ነጭም፣ ባሪያውና ነፃው፤ ሴትና ወንድ" (፪ ኔፊ ፳፮፤ ፴፫)። በቤተክርስቲያኗ ታሪክ በሙሉ፣ የእያንዳንዱ ዘረ አባል የሆኑ የብዙ ሀገሮች ሰዎች ተጠምቀዋል እናም እንደ ቤተክርስቲያኗ ታማኝ አባላት ኖረዋል። በጆሴፍ ስሚዝ ህይወት ውስጥ፣ አንዳንድ ጥቁር ወንድ አባላት በክህነት ተሾመው ነበር። በታሪኳ መጀመሪያ፣ የቤተክርስቲያኗ መሪዎች ከአፍሪካ ትውልድ ለሆኑ ወንድ አባላት ክህነትን መስጠት አቆሙ። የቤተክርስቲያኗ መዝገቦች የዚህ ልምድን መጀመሪያ ምን እንደሆነ ምንም አስተያየት አይሰጡም። የቤተክርስቲያኗ መሪዎች ይህን ልምድ ለመቀየር የእግዚአብሔር ራዕይ አስፈላጊ መሆኑን አምነው ነበር እናም በጸሎት መመሪያን ፈለጉ። ራዕይም ለፕሬዘደንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምባል መጣ እናም በሰኔ ፩፣ ፲፱፻፸፰ (እ.አ.አ.) ለሌሎች የቤተክርስቲያኗ መሪዎች ይህም ተረጋግጦ ነበር። ራዕዩም በክህነት ላይ በዘር ምክንያት የሚገድበውን በሙሉ እንዲወገድ አደረገ።

ለሚመለከተው ሁሉ፥

በመስከረም ፴፣ ፲፱፻፸፰ (እ.አ.አ.)፣ በ፲፱፻፸ኛው የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን የአመቱ ግማሽ አጠቃላይ ጉባኤ ላይ በቤተክርስቲያኗ ቀዳሚ አመራር የመጀመሪያ አማካሪ ፕሬዘደንት ኤን ኤልደን ታነር የሚቀጥለው ቀረበ፥

በዚህ አመት ሰኔ መጀመሪያ ላይ፣ ክህነትን እና የቤተመቅደስ በረከቶችን ለሁሉም ብቁ የቤተክርስቲያን አባላት ሁሉ ስለመስጠት ፕሬዘደንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምባል ራዕይ ተቀብለው እንደነበር ቀዳሚ አመራር አስታወቁ። በቅዱስ ቤተመቅደስ በተቀደሰ ክፍሎች ውስጥ ከረጅም ጥልቅ ሀሳብ እና ጸሎት በኋላ የመጡላቸውን ይህን ራዕይ ከተቀበሉ በኋላ፣ ይህን ለተቀበሉት እና ለተስማሙት አማካሪዎቻቸው እንዳቀረቡ ለጉባኤው እንድ ነግር ፕሬዘደንት ኪምባል ጠይቀውኝ ነበር። ከዚያም ይህ ለአስራ ሑለቱ ሐዋርያት ቡድን ቀረበ፣ እነርሱም በአንድ ድምፅ ተስማሙበት፣ እና በኋላም ለሁሉም አጠቃላይ ባለስልጣናት ቀረበ፣ እነርሱም በተመሳሳይ ሁኔታ በአንድ ድምፅ ተስማሙበት።

ፕሬዘደንት ኪምባል አሁን ይህን ደብዳቤ እንዳነብ ጠይቀውኛል፥

ሰኔ ፯ ቀን ፲፯፻፸፰
በአለም አቀፍ ለኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አጠቃላይ እና የአካባቢ የክህነት ሀላፊዎች ሁሉ፥

ውድ ወንድሞች፥

የጌታ ስራ በምድር ላይ ሲያድግ በምስክርነቱን ስናይ፣ የብዙ ሀገሮች ህዝብ ዳግም የተመለሰውን የወንጌል መልእክት ስለተቀበሉ፣ እና ዘወትር በሚያድግ ቁጥሮች በቤተክርስቲያኗ አባል ስለሆኑ ምስጋና አለን። ይህም በተራው ወንጌሉ የሚያቀርባቸውን ሁሉንም መብቶች እና በረከቶች ለእያንዳንዱ ብቁ የቤተክርስቲያን አባላት ለማቅረብ ያለንን ፍላጎት አነሳስቶናል።

አንድ ቀን በእግዚአብሔር ዘለአለማዊ አላማ ብቁ የሆኑት ወንድሞቻችን ሁሉ ክህነትን እንደሚቀበሉ ከእኛ በፊት የነበሩት የቤተክርስቲያኗ ነቢያት እና ፕሬዘደንቶች የሰጡትን የተስፋ ቃል እያወቅን፣ እና ከክህነት ስልጣን ተወግደው የነበሩትን ታማኝነት ምስክር በመሆን፣ ብዙ ሰዓቶችን በቤተመቅደሱ ታላቅ አዳራሽ ውስጥ ጌታን ለመለኮታዊ አመራር በመለመን ለረጅም ጊዜ እና በቅንነት ለእነዚህ ታማኝ ወንድሞቻችን ለምነን ነበር።

ጸሎታችንን ሰምቷል፣ እና በራዕይም እያንዳንዱ ታማኝ፣ ብቁ ወንድ ሰው በቤተክርስቲያኗ ውስጥ፣ መለኮታዊ ስልጣኑን ለመጠቀም ካለው ሀይል ጋር፣ ቅዱስ ክህነትን ለመቀበል እና ከቤተመቅደስ በረከት በተጨማሪ፣ ከሚወዳቸው ጋር ከዚያ የሚፈሱትን እያንዳንዱን በረከት እንዲደሰቱ ለረጅም ጊዜ ቃል የተገባለት ቀንም እንደደረሰ አረጋግጧል። በዚህም መሰረት፣ የቤተክርስቲያኗ ብቁ ወንድ አባላት ለዘር ወይም ቀለም ትኩረት ሳይሰጥ ወደክህነት ስልጣን ሊሾሙ ይችላሉ። የክህነት መሪዎችም ለዚህ ለአሮናዊ ወይም ለመልከ ጼዴቅ ክህነት ሹመት ተመራጭ ለሆኑት ሁሉ ለብቁነት የተመሰረተውን መሰረቶች እንደሚያሟሉ ለማረጋገጥ የጥንቃቄ ቃል ጥያቄ አመራርን እንዲከተሉ ታዝዘዋል።

ጌታ በአለም ውስጥ ሁሉ ያሉትን የባለስልጣን አገልጋዮቹን ድምፅ የሚያዳምጡትን እና የወንጌል እያንዳንዱ በረከቶችን ለመቀበል ራሳቸውን የሚያዘጋጁ ልጆቹን ለመባረክ ያለውን ፍላጎት እንዳስታወቀ በትጋት እናውጃለን።

በቅንነት የእናንተው፣

ስፔንሰር ደብሊው ኪምባል
ኤን ኤልደን ታነር
ሜሪዮን ጂ ሮምኒ

ቀዳሚ አመራር

ስፔንሰር ደብሊው ኪምባልን እንደ ነቢይ፣ ገላጭ፣ እና ባለራዕይ፣ እና እንደኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ፕሬዘደንት በመቀበል፣ እኛ እንደ አባል ተሰብሳቢዎች ይህን ራዕይ እንደ ጌታ ቃል እና ፈቃድ እንድንቀበል ቀርቦልናል። ይህን የሚቀበሉ ቀኝ እጃቸውን በማንሳት ያሳዩ። የሚቃወሙም በዚህ አይነት ምልክት።

ይህ የቀረበው ሀሳብ በአንድ ድምፅ ምርጫ በአዎንታዊነት ተደግፏል።

ሶልት ሌክ ስቲ፣ ዩታ፣ መስከረም ፴ ቀን ፲፱፻፳፰ (እ.አ.አ.)።

የታላቅ
ዋጋ ዕንቁ

ከየኋለኛው ቀን ቅዱሳን
የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን
የመጀመሪያ ነቢይ፣ ገላጭ፣ እና ባለራዕይ
ጆሴፍ ስሚዝ

ራዕያት፣ ትርጉም፣ እና ትረካ የተመረጡ።

ማውጫዎች

መግቢያ 5

ሙሴ . . . . . ፩

አብርሐም . . . . . ፳፯

ፍጹም ትክክለኛ ቅጂ ፩. . . . . ፳፯

ፍጹም ትክክለኛ ቅጂ ፪. . . . . ፴፤

ህዝቦች ግን ረግሜአለሁ።

፳፩ እንዲህም ሆነ ጌታ ለሔኖክ የምድርን
ነዋሪዎችን በሙሉ አሳየው፤ ፅዮን ከጊዜ
በኋላ ወደ ሰማይ [ሁ]እንደምትወሰድም ተመ
ለከተ አስተዋለም። እና ጌታም ለሔኖክ
እንዲህ አለው፥ እነሆ ለዘለአለም መኖሪ
ያዬ ትሆናለች።

፳፪ ሔኖክም ደግሞም የቀሩትን የአዳም
ልጆች የሆኑትን ህዝቦች አየ፤ እና እነር
ሱም ከቃየን ዘሮች በስተቀር ሁሉም የአ
ዳም ልጆች ድብልቆች ነበሩ፣ የቃየን ዘሮች
[ሂ]ጥቁር ነበሩ፣ እና ከእነርሱ መካከል ስፍራ
አልነበራቸውምና።

፳፫ ከዚያም በኋላ ፅዮን ወደ [ሁ]ሰማይ ተወ
ሰደች፣ እናም የምድርም ሀገሮች [ሃ]ሁሉም
ከእርሱ ፊት እንደነበሩ ሔኖክ [ሄ]አየ አስ
ተዋለም፤

፳፬ እና በትውልድ ላይ ትውልድም
መጣ፤ እና ሔኖክም [ሁ]ከፍ ብሎ ወደላይ ተነ
ስቶ ነበር፣ እንዲሁም በአብና በሰው ልጅ
እቅፍ ውስጥም ነበር፤ እና እነሆ፣ የሰይጣን
ሃይል በምድር ፊት ሁሉ ላይ ነበር።

፳፭ እና መላእክት ከሰማይ ሲወርዱም
አየ፤ እና ታላቅ ድምፅ እንዲህ ሲል ሰማ፥
በምድር ለሚኖሩት ወዮ፣ ወዮ።

፳፮ ሰይጣንንም አየ፤ እና በእጁም ታላቅ
[ሁ]ሰንሰለት ነበረው፣ እና ይህም ምድርን
በሙሉ [ሃ]በጭለማ ሸፈነ፤ እርሱም ቀና ብሎ
ሳቀ፣ እና የእርሱም [ሄ]መላእክት ተደሰቱ።

፳፯ እና ሔኖክ [ሁ]መላእክት የአብና ወልድ
[ሃ]ምስክር ይዘው ከሰማይ ሲወርዱ አየ፤ እና
መንፈስ ቅዱስ በብዙዎች ላይ አረፈ፣
እና እነርሱም በሰማይ ሀይሎች ወደ ፅዮን
አረጉ።

፳፰ እንዲህም ሆነ እግዚአብሔር የቀሩ
ትን ህዝቦች ተመለከተ፣ እናም አለቀሰ፤
ስለዚህም ሔኖክ እንዲህ ብሎ መሰከረ፥
ለምንድን ነው ሰማያት የሚያለቅሱት፣ እና
እምባቸውን እንደ ዝናብ በተራራው ላይ
እንደሚፈስ የሚያደርጉት?

፳፱ እና ሔኖክ ለጌታ እንዲህ አለ፥ ቅዱስ
እና ከዘለአለም ሁሉ እስከ ዘለአለም ሆነህ፣
ለምንድን ነው [ሁ]የምታለቅሰው?

፴ እና የዚህን ምድር፣ አዎን፣ እንደ
ዚህ አይነት ሚልዮን [ሁ]ምድሮችን፣ ታናሽ
መጠንን ሰው ለመቁጠር የሚችሉ ቢሆ
ንም፣ አንተ [ሃ]ለፈጠርካቸው የመቆጠሪያ
መጀመሪያም አይሆንም፤ እና መጋረጃህ
አሁንም ተወጥሯል፤ ነገር ግን አንተ እዚህ
አለህ፣ እና እቅፍህም እዚህ አለ፤ ደግሞም
አንተ ጻድቅ ነህ፤ ለዘለአለምም ሩህሩህና
ደግ ነህ፤

፴፩ እና ከዘለአለም እስከ ዘለአለም፣
ከፍጥረታትህ ሁሉ፣ ወደ እቅፍህም ፅዮ
ንን ወስደሀል፤ እና የዙፋንህ ነዋሪዎችም
[ሁ]ከሰላም፣ [ሃ]ከፍትህ፣ እና [ሄ]ከእውነት ሌላ
ነዋሪዎች የላቸውም፤ ምህረት በፊት ለፊ
ትህ ይሄዳል እና መጨረሻ የለውም፤ አንተ
ለማልቀስ እንዴት ትችላለህ?

፴፪ ጌታም ለሔኖክ እንዲህ አለው፥
እነሆ፣ እነዚህ ወንድሞችህን እይ፤ እነርሱ
[ሁ]የእጅህ ስራዎች ናቸው፣ እና በፈጠርኳ
ቸው ቀንም [ሃ]እውቀታቸውን ሰጠኋቸው፤
እና በዔደን ገነትም ለሰው [ሄ]ነጻ ምርጫውን
ሰጠሁት።

፳ ሀ ሙሴ ፤፡፡ ፳፪–፳፫።
ቅ.መ.መ. አዲሲቱ
ኢየሩሳሌም።
፳፩ ሀ ሙሴ ፤፡ ፳፬።
፳፪ ሀ ፪ ነፊ ፳፯፡ ፴፫።
፳፫ ሀ ቅ.መ.መ. ሰማይ።
ለ ት.እና ቃ. ፹፰፡ ፻፯፤
ሙሴ ፩፡ ፳፯–፳፱።
ሐ ቅ.መ.መ. ራዕይ።

፳፬ ሀ ፪ ቆሮ. ፲፪፡ ፩–፬።
፳፭ ሀ አልማ ፲፪፡ ፲–፲፩።
ለ ኢሳ. ፳፡ ፩–፪።
ሐ ይሁዳ ፩፡ ፤፣
ት.እና ቃ. ፳፱፡ ፴፯–፴፯።
፳፮ ሀ ቅ.መ.መ. መላእክት።
ለ ቅ.መ.መ. ምስክርነት።
፳፱ ሀ ኢሳ. ፳፫፡ ፯–፲።
፴ ሀ ት.እና ቃ. ፫፭፡ ፳፬፤
ሙሴ ፩፡ ፴፫።
ለ ቅ.መ.መ. መፍጠር፣
ፍጥረት።
፴፩ ሀ ቅ.መ.መ. ሰላም።
ለ ቅ.መ.መ. ፍትህ።
ሐ ቅ.መ.መ. እውነት።
፴፪ ሀ ሙሴ ፩፡ ፴።
ለ ቅ.መ.መ. እውቀት።
ሐ ቅ.መ.መ. ነጻ ምርጫ።

፴፫ እና ለወንድሞችህም ይህን ብያለሁ፣ እና ደግሞም እርስ በርስ እንዲዋደዱ፣ እና እኔ አባታቸውን ይመርጡ ዘንድ ትእዛዝን ሰጠኋቸው፤ ነገር ግን እነሆ፣ እነርሱ [ሀ]ፍቅር የላቸውም፣ እና የራሳቸውንም ደም ይጠላሉ፤

፴፬ [ሀ]የእሳት አይነት ቁጣዬም እነርሱ ላይ ተቀጣጥሏል፤ እና በእነርሱም ላይ ቁጣዬ ታላቅ ስለሆነ፣ በቅያሜዬም [ለ]የጥፋት ውሀ እልክባቸዋለሁ፣ ጥብቅ ቁጣዬም በእነርሱ ላይ ተቀጣጠላለችና።

፴፭ እነሆ፣ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ስሜም የቅድስና [ሀ]ሰው ነው፤ የምክር ሰውም ስሜ ነው፤ እና መጨረሻ የሌለውና ዘለአለማዊም ደግሞ [ለ]ስሜ ነው።

፴፮ ስለዚህ፣ እጆቼን እዘረጋለሁ እና የፈጠርኳቸውን ፍጥረታት ሁሉ ልይዛቸውም እችላለሁ፤ እና ደግሞም [ሀ]አይኔ ሊበሳቸው ይችላል፣ እና በእጆቼ ከሰራኋቸው ፍጥረታት ሁሉ ከወንድሞችህ ውስጥ እንዳለው እንደእነዚህ አይነት [ለ]ጥፋቶች አልነበሩም።

፴፯ ነገር ግን እነሆ፣ ኃጢአታቸው በአባቶቻቸው ጭንቅላት ላይ ይሆናል፤ ሰይጣንም አባታቸው ይሆናል፣ ጣርም እጣቸው ይሆናል፤ እናም ሰማያትም በሙሉ ለእነርሱ፣ እንዲሁም በእጆቼ ለሰራኋቸው በሙሉ፣ ያለቅሳሉ፤ ስለዚህ እነዚህ እንደሚሰቃዩ ሲያዩ፣ ሰማያት አያለቅሱም?

፴፰ ነገር ግን እነሆ፣ እነዚህ በአይንህ ያየሀቸውም በጎርፍ ይጠፋሉ፤ እና እነሆ፣ እኔ እዘጋቸዋለሁ፤ [ሀ]እስር ቤት ለእነርሱ አዘጋጅቼላቸዋለሁ።

፴፱ እና [ሀ]ያ የመረጥኩትም በፊቴ ለምኗል። ስለዚህ፣ ለኃጢአታቸው ተሰቃየ፤ ንስሀ ከገቡም በዚያ ቀን [ለ]የመረጥኩት ወደ እኔ ይመለሳሉ፣ እና እስከዚያም ቀን ድረስ [ሐ]በስቃይ ውስጥም ይሆናሉ፤

፵ ስለዚህ፣ ለዚህም ሰማያት፣ አዎን፣ እና በእጆቼ የሰራኋቸውም ሁሉ ያለቅሳሉ።

፵፩ እንዲህም ሆነ ጌታ ሔኖክን አነጋገረው፣ እና ስለሰው ልጆች ድርጊቶች ሁሉም ነገረው፤ ስለዚህ ሔኖክ አወቀ፣ እና ጥፋታቸውንና ስቃያቸውን አየ፣ እና አለቀሰ እናም ክንዶቹን ዘረጋ፣ [ሀ]ልቡም እንደ ዘለአለም ተጉረበረበ፤ እና አንጀቱም በጥልቅ ተነካ፤ እናም ዘለአለምም ተንቀጠቀጠች።

፵፪ ሔኖክም [ሀ]ኖህንና [ለ]ቤተሰቡን አየ፤ የኖህ ልጆች ዘሮችም በጊዜያዊ ደህንነት ይድናሉ፤

፵፫ ስለዚህ ሔኖክ ኖህ [ሀ]መርከብን እንደሰራም አየ፤ እና ጌታም ፈገግ አለበት፣ እና በእጁም ያዘው፤ ነገር ግን በቀሩት ጥፋተኞች ላይ ጎርፎቹ መጡ እና አጥለቀለቋቸው።

፵፬ ሔኖክም ይህን ተመለከተ፣ የነፍስ መራራነት ተሰማው፣ እና ለወንድሞቹ በማልቀስ ለሰማያት እንዲህ አለ፥ ለመጽናናት [ሀ]እምቢ እላለሁ፤ እግዚአብሔር ግን ሔኖክን አለው፥ ልብህን አንሳ፣ ተደሰትም፤ እና ተመልከት።

፵፭ እንዲህም ሆነ ሔኖክ ተመለከተ፤ እና ከኖህ ጀምሮ የምድርን ቤተሰቦች አየ፤ እና ለጌታ እንዲህ ብሎ ጮኸ፥ የጌታ ቀን መቼ ይመጣል? የሚያለቅሱት ሁሉ

፴፫ ሀ ቅ.መ.መ. ፍቅር።
፴፬ ሀ ኢሳ. ፴፥፳፯፤
ናሆ ፩፥፮፤
ት. እና ቃ. ፴፭፥፲፬።
ለ ዘፍጥ. ፯፥፬፤ ፲፤
ሙሴ ፰፥፲፯፣ ፳፬።
ቅ.መ.መ. የኖኅ ዘመን
የጥፋት ውሀ።
፴፭ ሀ ሙሴ ፮፥፶፯።
ለ ሙሴ ፩፥፫።
፴፮ ሀ ት. እና ቃ. ፴፰፥፪፤
፹፰፥፵፩፤
ሙሴ ፩፥፴፭–፴፯።
ለ ዘፍጥ. ፮፥፭–፮፤
ሙሴ ፰፥፳፪፣ ፳፰–፴።
፴፰ ሀ ፩ ጴጥ. ፫፥፲፰–፳።
ቅ.መ.መ. ሲኦል።
፴፱ ሀ ይህም አዳኝ ማለት ነው።
ለ ሙሴ ፬፥፪፤
አብር. ፫፥፳፯።
ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ።
ሐ ቅ.መ.መ. ኩነኔ።
፵፩ ሀ ሞዛያ ፳፰፥፫።
ቅ.መ.መ. ርህራሄ።
፵፪ ሀ ቅ.መ.መ. ኖኅ፣ የመፅሐፍ
ቅዱስ የአባቶች አለቃ።
ለ ሙሴ ፰፥፲፪።
፵፫ ሀ ዘፍጥ. ፮፥፲፬–፲፮፤
ኤተር ፮፥፯።
፵፬ ሀ መዝ. ፸፯፥፪፤
ኤተር ፲፭፥፫።

ᵐእንዲቀደሱና ዘለአለማዊ ህይወት ይኖራቸው ዘንድ፣ የጻድቁ ደምስ መቼ ነው የሚፈሰው?

፶፯ ጌታም እንዲህ አለ፡ ይህም ᵐበመካከለኛው ዘመን፣ በጥፋትና በበቀል ቀናት ነው።

፶፰ እና እነሆ፣ ሔኖክም የሰው ልጅ በስጋ የሚመጣበትን ቀን አየ፤ እና መንፈሱም በመደሰት እንዲህ አለ፡ ጻድቁ ወደላይ ተነስቷል፣ እናም ከምድር መሰረት ጀምሮም ᵐበጉ ተገድሏል፤ እና በእምነትም በኩል በአብ እቅፍ ውስጥ ነኝ፣ እና እነሆ፣ ᵃፅዮንም ከእኔ ጋር ነች።

፶፱ እንዲህም ሆነ ሔኖክ ᵐምድርን ተመለከተ፤ እና ከጥልቁም እንዲህ የሚል ድምጽ ሰማ፡ ወዮ፣ ለእኔም ለሰው እናት ወዮለኝ፤ በልጆቼ መጥፎነት ምክንያት አሞኛል፣ ደክሞኛልም። መቼ ᵃአርፋለሁ፣ እና ከእኔ ውስጥ ከወጡት ᵃᵃእድፍ እነጻለሁን? አርፍስ ዘንድ ፈጣሪዬ መቼ ይቀድሰኛል፣ ለዘመንም በፅድቅ በፊቴ መቼ ይኖራል?

፷ ሔኖክ ምድር ስታለቅስ ሲሰማም አለቀሰ፣ እና ለጌታም እንዲህ ብሎ ጮኸ፡ ጌታ ሆይ፣ በምድር ላይ ርህራሄ አይኖርህምን? የኖህንን ልጆችንስ አትባርክም?

፷፩ እንዲህም ሆነ ሔኖክ ወደጌታ መጮሁን እንዲህ በማለት ቀጠለ፡ ጌታ ሆይ፣ በአንድያ ልጅህ፣ እንዲሁም በኢየሱስ ክርስቶስ፣ ስም ለኖህና ለዘሩ ርህራሄ ይኖርህ ዘንድ፣ መሬትም በመጥፊያው ውሀ ደግሞም እንዳትሸፈን ዘንድ እጠይቅሀለሁ።

፷፪ ጌታም ይህን ሊከለክለው አልቻለም፤ ከሔኖክ ጋር ቃል ገባ፣ እና ከእርሱም ጋር ቃለ መሀላ ᵐኅርፉን እንደሚያቆም፤ የኖህ ልጆችንም እንደሚጠራቸው ማለለት።

፷፫ ከዚያም ምድር እስካለች ድረስ የእርሱ ᵐየሚቀሩት ዘሮችም በሁሉም ህዝቦች መካከል ይገኙ ዘንድ የማይቀየር አዋጅን ሰደደ።

፷፫ እና ጌታም እንዲህ አለ፡ በዘሩ በኩል ᵐመሲህ የሚመጣበት የተባረከ ነው፤ ምክንያቱም እንዳለው—እኔ የፅዮን ᵃንጉስ፣ እንደ ዘለአለም ሰፊ የሆነው የሰማይ ᵃᵃአለት፣ መሲህ ነኝ፣ እና ማንም በበሩ ገብተው ወደ እኔ ᵐየሚወጡትም አይወድቁም፤ ስለዚህ፣ የተናገርኩባቸውም የተባረኩ ናቸው፣ ከዘለአለም ደስታ ᵐመዝሙር ጋር በደስታ ይመጣሉና።

፷፬ እንዲህም ሆነ ሔኖክ ወደጌታ እንዲህ ብሎ ጮኸ፡ የሰው ልጅ በስጋ ሲመጣ፣ ምድርም ታርፋለችን? እነዚህን ነገሮች እንድታሳየኝ እለምንሀለሁ።

፷፭ ጌታም ለሔኖክ አለው፣ ተመልከት፣ እና ተመለከተ፣ እና ᵐየሰው ልጅን እንደ ሰው ᵃበመስቀል ላይ ሲሰቀልም አየ እና ተመለከተ።

፷፮ የደመቀ ድምጽንም ሰማ፤ እና ሰማያት ተሸፍነው ነበር፤ እና የእግዚአብሔር ፍጥረታት ሁሉ አዘኑ፤ ምድርም ᵐአቃሰተች፤ ድንጋዮችም ተሰነጠቁ፤ ቅዱሳንም ᵃተነሱ፣ እና በሰው ልጅ ᵃᵃቀኝ እጅም በክብር ᵐዘውዶች ተጫኑ።

፷፯ እና ᵐበእስር ቤት የነበሩትም ሁሉ ᵃመንፈሶች መጡ፣ እና በእግዚአብሔር ቀኝ እጅ በኩል ቆሙ፤ እና የቀሩትም እስከ ታላቁ የፍርድ ቀን ድረስ በጭለማ ሰንሰለቶች ታሰሩ።

፷፰ ሔኖክም እንደገና አለቀሰ እና ለጌታ

፷፭ ሀ ቅ.መ.መ. ቅድስና።
፷፮ ሀ ሙሴ ፭፡ ፱፯።
፷፯ ሀ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር በግ።
ለ ሙሴ ፲፡ ፳፭።
፷፰ ሀ ቅ.መ.መ. ምድር—ምድርን ማፅዳት።
ለ ሙሴ ፲፡ ፱፱፣ ፻፳፣ ፳፬።
ሐ ቅ.መ.መ. እድፍ፣ እድፍነት።
፷፭ ሀ መዝ. ፻፱፡ ፲–፱።
፷፮ ሀ ሙሴ ፳፡ ፪።
፷፯ ሀ ቅ.መ.መ. መሲህ።
ለ ማቴ. ፪፡ ፪፣ ፪ ኔፊ ፲፡ ፲፱፣ አልማ ፭፡ ፶፣ ት.እና ቃ. ፻፳፳፡ ፳፪።
ሐ መዝ. ፫፭፡ ፲፣ ፫፳፡ ፴፭፣ ሔለ. ፭፡ ፲፪። ቅ.መ.መ. አለት።
መ ፪ ኔፊ ፴፭፡ ፲፱–፳።
ሠ ቅ.መ.መ. መዝሊታ።
፷፭ ሀ ቅ.መ.መ. የሰው ልጅ።
ለ ፫ ኔፊ ፳፯፡ ፲፡ ቅ.መ.መ. መሰቀል።
፷፮ ሀ ማቴ. ፳፯፡ ፶፭፣ ፻–፻፭።
ለ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
ሐ ማቴ. ፳፭፡ ፴፡ መ ቅ.መ.መ. አክሊል፤ ከፍተኛነት።
፷፯ ሀ ት.እና ቃ. ፫፯፡ ፫፭–፫፡ ፲፫፡ ፻፱።
ለ ቅ.መ.መ. መንፈስ።

ከተማ፣ ወገባቸውን እንዲታጠቁ እና ለእኔ መመለሻ ወደፊት ይጠብቁ ዘንድ ፡እንዲሰ በሰቡ አደርጋለሁ፤ በዚያም ድንኳኔም ይገ ኛልና፣ እና ይህችም ፅዮን፣ ᵃአዲስቷ ኢየ ሩሳሌም ተብላ ትጠራለች።

፷፫ ጌታም ለሔኖክ እንዲህ አለው፡ አን ተና ᵇከተማህ ሁሉ በዚያ ትገናኛቸዋለህ፣ እናም በእቅፋችንም እንቀበላቸዋለን፣ እነ ርሱም ያዩናል፤ እና አንገታቸውን እናቅፋ ለን፣ እና እነርሱም አንገታችንን ያቅፋሉ፣ እና እንሳሳማለን፤

፷፬ እኔም በዚያ መኖሪያዬ ይሆናል፣ እና ከፈጠርኳቸው ሁሉ ውስጥ የምትመጣው ፅዮን ትሆናለች፤ እና ለአንድ ᵇሺ አመታ ትም ምድር ᵃታርፋለች።

፷፭ እንዲህም ሆነ ሔኖክ በኋለኛዎቹ ቀናት ለአንድ ሺህ አመታት በፅድቅ በም ድር ለመኖር የሰው ልጅ ᵇየሚመጣበትን ቀናት አየ፤

፷፮ ከዚያ ጊዜ በፊት ግን ከመጥፎዎቹ መካከል ታላቅ ስቃይን አየ፤ እና ባህርም እንደተቸገረ አየ፣ እና በመጥፎው ላይ የሚ መጣውን የሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔርን ᵇፍርድ በመፍራት ወደፊት እየተመለከቱ የሰዎች ልብ ᵃሲወድቁባቸው ተመለከተ።

፷፯ ጌታም ለሔኖክ ሁሉንም ነገሮች፣ እንዲሁም እስከ አለም መጨረሻ ድረስ አሳየው፤ እና የፅድቅን ቀን፣ የቤዛነታቸ ውንም ሰአት አየ፣ እና ᵇየደስታ ሙላትን ተቀበለ፤

፷፰ እና ᵇየፅዮን ቀናት ሁሉ፣ በሔኖክ ቀናት፣ ሶስት መቶ ስልሳ አምስት ነበሩ።

፷፱ እና ሔኖክና ሁሉም ህዝቡ ከእግዚአ

፷ ᵇ ቅ.መ.መ. የመጨረሻ ቀናት፣ የኋለኛው ቀናት።

፷፩ ᵇ ቅ.መ.መ. ምድር—የምድር የመጨረሻ ሁኔታ።

ᵃ ት. እና ቃ. ፴፯፡፲፩–፲፪፤ ፹፪፡፳፫፣

ᵇ ሐ ቅ.መ.መ. ዐይነ-እርግብ።

መ ፩ ኔፊ ፳፪፡፲፩–፳፪፤ ፪ ኔፊ ፴፡፲።

፷፪ ᵇ መዝ. ፹፭፡፲፩። ቅ.መ.መ. የወንጌል ዳግም መመለስ።

ᵃ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።

ᵇ ሐ ቅ.መ.መ. ምስክርነት።

መ ቅ.መ.መ. መፅሐፈ ሞርሞን።

ᵐ ኢሳ. ፷፱፡፪።

ᵈ ቅ.መ.መ. እስራኤል—የእስራኤል መስብሰብ።

ᵉ ቅ.መ.መ. አዲሲቱ ኢየሩሳሌም።

፷፫ ᵇ ራዕ. ፳፩፡፱–፲፩፤ ት. እና ቃ. ፴፭፡፲፩–፲፪፤ ሙሴ ፯፡፲፱–፷፩።

፷፬ ᵇ ቅ.መ.መ. አንድ ሺህ አመት።

ᵃ ሙሴ ፯፡፴፯።

፷፭ ᵇ ይሁዳ ፩፡፲፱። ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።

፷፮ ᵇ ቅ.መ.መ. ፍርድ፣ የመጨረሻው።

ᵃ ኢሳ. ፲፫፡፭–፮።

፷፯ ᵇ ቅ.መ.መ. ደስታ።

፷፰ ᵇ ዘፍጥ. ፭፡፳፫፣ ሙሴ ፰፡፩።

ብሔር ጋር ᵐተራመዱ፣ እና እርሱም በፅዮን መካከል ኖረ፤ እንዲህም ሆነ ፅዮንም አል ነበረችም፣ እግዚአብሔር ወደ እቅፉ ተቀ ብሏታልና፤ እና ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ፅዮን ጠፋች የሚል አባባል ነበር።

ምዕራፍ ፳

[የካቲት ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.)]

ማቱሳላ ተነበየ—ኖህና ልጆቹ ወንጌልን ሰበኩ—ታላቅ ጥፋት በዛ—ወደ ንስሀ መጠራትም አልተሰማም—እግዚአብሔ ርም ሰጋዎችን በሙሉ በጥፋት ውሀ ለማ ጥፋት አወጀ።

፩ ሄኖክም የኖረበት ቀናት ሁሉ አራት መቶ ሰላሳ ዓመት ነበሩ።

፪ እንዲህም ሆነ የሔኖክ ልጅ ᵐማቱሳላም የጌታ ቃል ኪዳን ይሟላ ዘንድ አልተወሰ ደም ነበር፤ በእውነትም ኖህ የወገቡ ፍሬ እንደሚሆን ቃል ገብቶለት ነበርና።

፫ እንዲህም ሆነ ማቱሳላም ከወገቡ (በኖህ በኩል) የአለም መንግስታት ሁሉ እንደሚ መጡም ተነበየ፣ እና በራሱም ላይ ክብ ርን ወሰደ።

፬ እና በምድር ላይ ታላቅ ርሀብ መጣ፣ እና ጌታም ምድርን በታላቅ ርግማን ረገ መው፣ እና በዚያም ብዙ ፍሪዎቹም ሞቱ።

፭ እንዲህም ሆነ ማቱሳላም መቶ ሰማንያ ሰባት ዓመት ኖረ፣ ላሜሕንም ወለደ፤

፮ ማቱሳላም ላሜሕን ከወለደ በኋላ የኖ ረው ሰባት መቶ ሰማንያ ሁለት ዓመት ሆነ፤ ወንዶችንም ሴቶችንም ወለደ፤

፯ ማቱሳላም የኖረበት ዘመን ሁሉ ዘጠኝ መቶ ስልሳ ዘጠኝ ዓመት ሆነ፤ ሞተም።

፰ ላሜሕም መቶ ሰማንያ ሁለት ዓመት ኖረ፣ ልጅንም ወለደ፣

፱ ስሙንም እግዚአብሔር ᵐበረገማት ምድር ከተግባራችንና ከእጅ ሥራችን ይህ ያሳርፈናል ሲል ᵃኖኅ ብሎ ጠራው።

፲ ላሜሕም ኖኅን ከወለደ በኋላ የኖረው አምስት መቶ ዘጠና አምስት ዓመት ሆነ፤ ወንዶችንም ሴቶችንም ወለደ።

፲፩ ላሜሕ የኖረበት ዘመን ሁሉ ሰባት መቶ ሰባ ሰባት ዓመት ሆነ፤ ሞተም።

፲፪ ኖህም በአራት መቶ ሀምሳ አመቱ ያፌትን ᵐወለደ፤ እና ከአርባ ሁለት አመት በኋላ ᵃሴምን ከያፌት እናት ወለደ፣ እናም በአምስት መቶ አመቱም ᵇካምንን ወለደ።

፲፫ ᵐኖህና ልጆቹም ጌታን ᵃአደመጡ፣ እና ምክሩንም ተቀበሉ፣ እና የእግዚአብ ሐርም ᵇልጆች ተብለው ተጠሩ።

፲፬ እነዚህ ወንዶች በምድር ገፅ ላይ እየ ተባዙ ሄዱ፣ እና ሴት ልጆችም ለእነርሱ ተወለዱላቸው፣ የሰው ᵐወንዶችም እነዚህ ሴት ልጆች ቆንጆ እንደሆኑ አዩ፣ እና እንደ ፍላጎታቸውም እነዚህን ሚስቶቻቸው አደ ረጓቸው።

፲፭ ጌታም ለኖህ እንዲህ አለው፥ የወንድ ልጆችህ ሴት ልጆች ራሳቸውን ᵐሸጠዋል፤ እነሆ፣ ቁጣዬ በሰው ልጆች ላይ ተቀጣጥላ ለች፣ ድምጼን አያደምጡምና።

፲፮ እንዲህም ሆነ ኖህም ተነበየ፣ እናም የእግዚአብሔርን ነገሮች፣ እንዲሁም በመ ጀመሪያው እንደነበረው፣ አስተማረ።

፲፯ ጌታም ለኖህ እንዲህ አለው፥ መን ፈሴ ከሰው ጋር ሁልጊዜም ᵐአይቆይም፣ እርሱ ሁሉም ᵃስጋ መሞት እንዳለበት ያው ቃልና፤ ነገር ግን እድሜው አንድ መቶ ሀያ

፳፱ ᵐ ዘፍጥ. ፭፡፳፯፤ ሙሴ ፮፡ ፴፬።
ᵃ ቅ.መ.መ. መራመድ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መራመድ (መሄድ)።
፳ ᵐ ቅ.መ.መ. ማቱሳላ።
ᵃ ᵐ ሙሴ ፬፡ ፳፫።
ᵇ ቅ.መ.መ. ኖኅ፣ የመፅሐፍ ቅዱስ የአባቶች አለቃ።
፲፪ ᵐ ዘፍጥ. ፭፡ ፴፪።
ᵃ ቅ.መ.መ. ያፌት።
ᵇ ቅ.መ.መ. ሴም።
ᵇ ቅ.መ.መ. ካም።
፲፫ ᵐ ት. እና ቃ. ፲፴፯፡ ፴፩።
ᵃ ቅ.መ.መ. ገብርኤል።
ᵇ ቅ.መ.መ. ታዛዥነት፣ ታዛዥ፣ መታዘዝ።
ᵇ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ወንድ እና ሴት ልጆች።
፲፬ ᵐ ሙሴ ፭፡ ፶፪።
ᵃ ᵐ ቅ.መ.መ. ጋብቻ፣ መጋባት—በሀይማኖቶች መካከል መጋባት።
፲፯ ᵐ ዘፍጥ. ፮፡ ፫፣ ፪ ኔፊ ፳፯፡ ፲፩፣ ኤተር ፪፡ ፲፩፣ ት. እና ቃ. ፩፡ ፴፫።
ᵃ ᵐ ፪ ኔፊ ፱፡ ፱።
ᵃ ቅ.መ.መ. ስጋ።

ይሆናል፤ እና ሰዎች ንስሀ ካልገቡ፣ ሐጎር ፉን እልክባቸዋለሁ።

፲፰ በዚያም ቀናት ᵇግዙፍ ሰዎች በምድር ላይ ነበሩ፣ እና ኖህን ለመግደልም ፈለጉ፤ ነገር ግን ጌታ ከኖህ ጋር ነበር፣ እና የጌታ ᵃሀይልም እርሱ ላይ አርፎ ነበር።

፲፱ ጌታ ᵇበስርዓቱም ᵃኖኅን ሾመው፣ እና፣ ለሔኖክ እንደተሰጠው፣ ወደ ሰው ልጆች እንዲሄድ እና ወንጌሉን ᶜእንዲሰ ብክ አዘዘው።

፳ እንዲህም ሆነ ኖህ የሰው ልጆች ᵇንስሀ እንዲገቡ ጠራቸው፤ ነገር ግን የእርሱን ቃላትን አላደመጡም።

፳፩ ደግሞም፣ ከሰሙትም በኋላ፣ ወደ ፊቱ መጥተው እንዲህ አሉ፥ እነሆ፣ እኛ የእግዚአብሔር ልጆች ነን፤ የሰውን ሴት ልጆች ለራሳችን አልወሰድንም? እና ᵇእየ በላን እየጠጣን፣ እና እያገባንና በጋብቻ እየ ሠጠን አይደለንምን? ሚስቶቻችንም ልጆ ችን ወልደውልናል፣ እና እነዚህም እንደ ቀደሙት ሰዎች የታወቁ ጠንካራ ሰዎች ናቸው። እና የኖህን ቃላት አላደመጡም።

፳፪ እግዚአብሔርም የሰዎች ᵇጥፋት በም ድር ላይ የበዛ እንደሆነ አየ፤ እና የእያንዳ ንዱ ሰው የልቡ ᵃሀሳብ ምኞትም ሁልጊዜ ፈጽሞ ክፉ ሆነ።

፳፫ እንዲህም ሆነ፣ ኖህም ለህዝቡ ᵇመስ በክን እንዲህ በማለት ቀጠለ፥ አድምጡ፣ እና የቃላቶቼን ምክር ተቀበሉ፤

፳፬ እንደ አባቶቻችሁም ᵇእመኑ ለኃ ጢአታችሁም ንስሀ ግቡ እና በእግዚአብ ሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ᵃተጠ መቁ፣ እና ሁሉንም ነገሮችን ᵃይገለፅላችሁ ዘንድ መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል ትችላ ላችሁ፤ እና ይህን ካላደረጋችሁ፣ የጥፋት ውሀ ይመጣባችኋል፤ ይህም ቢሆንም አላ ደመጡትም።

፳፭ ኖህም በዚህ ተጸጸተ፣ እናም በም ድር ላይ እግዚአብሔር ሰውን በመፍጠሩ ልቡ ተጨነቀ፣ እና ይህም ልቡን እጅግ አሳዘነው።

፳፮ ጌታም እንዲህ አለ፥ የፈጠርሁትን የሰው፣ ሰውና እንስሣት፣ ተንቀሳቃሾች ፍጡራን እስከ ሰማይ ወፎች፣ ከምድር ገፅ ᵇአጠፋለሁ፣ ስለፈጠርኳቸው እና ስለሰ ራኋቸው ኖህ ተጸጽቷልና፤ እና ህይወቱን ለማጥፋትም ስለሚፈልጉ እኔን ጠርቶኛል።

፳፯ እንዲሁም ኖህ በጌታ አይኖች ውስጥ ᵇፀጋን አገኘ፤ በዘመኑ ከነበሩት ሰዎች ሁሉ ይልቅ ᵃፍጹምና ከበደል የራቀ ሰው ነበር፤ እና ሶስቱ ልጆቹ ሴም፣ ካምንና ያፌት እን ዳደረጉት፣ ᵃአካሄዱንም ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ።

፳፰ ምድርም በእግዚአብሔር ፊት በክፉ ሥራ ᵇረከሰች፣ እናም በአመጽም ተሞል ታለች።

፳፱ እግዚአብሔር ምድርን ተመለከተ፣ እና እነሆ ረከሳ ሁሉም ስጋዎች ለባሽ አካ ሄዱን በምድር ላይ አበላሽቶ ነበርና።

፴ እግዚአብሔርም ኖህን እንዲህ አለው፥ የስጋ ለባሽ ሁሉ መጨረሻ በፊቴ መጥቷል፣ ምድርም በአመፅ ተሞልታለችና፣ እናም እነሆ ስጋን ሁሉ ከምድር ውስጥ ᵇአጠፋ ለሁ።

፲፯.ሐ ዘፍጥ. ፯፥፩፣ ፲፣
ሙሴ ፯፥ ፴፩።
፲፰ ሀ ዘፍጥ. ፮፥፩፣
ዘኁል. ፲፫፥ ፴፫፣
ኢ.ያ. ፲፯፥ ፲፭።
ለ ቅ.መ.መ. ሀይል።
፲፱ ሀ ቅ.መ.መ. የመልከ
ጼዴቅ ክህነት።
ለ አብር. ፩፥ ፲፱።
ሐ ት. እና ቃ. ፻፯፥ ፶፪።
ቅ.መ.መ. ሾመም፣ ሹመት።
መ ቅ.መ.መ. የሚስዮን ስራ።
፳ ሀ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣
ንስሀ መግባት።
፳፩ ሀ ማቴ. ፳፬፥ ፴፰–፴፱፣
ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፥ ፶፩።
፳፪ ሀ ዘፍጥ. ፮፥ ፭፣
ሙሴ ፯፥ ፴፯–፴፯።
ለ ሞዛያ ፩፥ ፴፣
አልማ ፲፪፥ ፲፩።
ቅ.መ.መ. ሀሳቦች።
፳፫ ሀ ቅ.መ.መ. መስበክ።
፳፩ ሀ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
ለ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣
መጥመቅ—ለመጠመቅ
ብቁነት።
ሐ ፪ ኔፊ ፴፪፥ ፪–፭።
፳፭ ሀ ቅ.መ.መ. ምድር—
ምድርን ማፅዳት።
፳፯ ሀ ቅ.መ.መ. ጸጋ።
ለ ዘፍጥ. ፮፥ ፱።
ሐ ቅ.መ.መ. መራመድ፣
ከእግዚአብሔር ጋር
መራመድ (መሄድ)።
፳፰ ሀ ዘፍጥ. ፮፥ ፲፩–፲፫።
፴ ሀ ት. እና ቃ. ፶፮፥ ፫።

ከመፅሐፈ አብርሐም ቅርፅ

ቁጥር ፩

መግለጫ

ስዕል ፩ የእግዚአብሔር መላእክት።
ስዕል ፪ አብርሐም በመሰዊያ ላይ ታስሮ።
ስዕል ፫ የኤልከናኽ የባእድ አምላኪ ቄስ አብርሐምን እንደ መስዋዕት ለማቀርብ ሲሞክር።
ስዕል ፬ የባእድ አምላክ ቀሳውስት መሰዊያ ድንጋይ ከኤልከናኽ፣ ሊብናኽ፣ ማህማርከራኽ፣ ቆራሽና ፈርዖን አማልክት ፊት ቆሞ።
ስዕል ፭ የባእድ አምላክ ኤልከናኽ።
ስዕል ፮ የባእድ አምላክ ሊብናኽ።
ስዕል ፯ የባእድ አምላክ ማህማርከራኽ።
ስዕል ፰ የባእድ አምላክ ቆራሽ።
ስዕል ፱ የባእድ አምላክ ፈርዖን።
ስዕል ፲ አብርሐም በግብፅ ውስጥ።
ስዕል ፲፩ ግብጻውያን እንደገባቸው፣ የሰማይ አምዶችን እንዲያስመስሉ የተመደቡ።
ስዕል ፲፪ ራኡኪያንግ፣ ከጭንቅላቶቻችን በላይ ያለውን ሰማይ ወይም ጠፈርን የሚያስመለክት፤ ነገር ግን በዚህ ሁኔታ፣ ከዚህ ርእሰ ጉዳይ በኩል፣ የአብራውያን ቃል፣ ሻኡማዩም፣ በመመለስ ግብጻውያን ሻኡማኡን፣ ከፍ ማለትን፣ ወይም ሰማያትን ለማስመልከት ያደረጉት ነው።

መፅሐፈ አብርሐም

በጆሴፍ ስሚዝ ከፓፓይረስ የተተረጎመ

ከግብፅ መቃብር ስፍራዎች በእጆቻችን ውስጥ ከገቡት አንዳንድ የጥንት መዛግብት ትር ጉም። መፅሐፈ አብርሐም ተብሎ የተጠራው፣ አብርሐም በግብፅ እያለ በፓፓይረስ ላይ በእራሱ እጆች የተጻፉ ፅሁፎች።

ምዕራፍ ፩

አብርሐም የፔትሪያርካዊ ስርዓት በረከትን ፈለገ—በከላውዴዎ ውስጥ በሐሰት ቀሳ ውስት ተንገላታ—ያህዌህ አዳነው—የግ ብፅ ጅማሬ መንግስትም ተከለሰ።

በ[a]አባቴ መኖሪያ [b]በከለዳውያን ምድር ውስጥ፣ እኔ [c]አብርሐም ሌላ [d]የመኖሪያ ስፍራን ማግኘት እንዳለብኝ አወቅሁኝ።

[e]፪ እና ታላቅ [f]ደስታና ሰላም እናም [g]እረ ፍት ለእኔ እንዳሉም ስላወቅሁኝ፣ የአባ ቶችን በረከቶች ለማግኘት እና ይህንንም ለማስተዳደር መብትም ለማግኘት ለመሾ ምም ፈለግሁኝ፤ [h]የጻድቅ ተከታይ በመ ሆኔ፣ እና ታላቅ [i]እውቀቶችን ለመረከብ፣ እናም ከዚህም በላይ ታላቅ ጻድቅ ተከታይ ለመሆን፣ እና ከዚህም ታላቅ የሆኑ እውቀ ቶችን ለመረከብ፣ እና የብዙ ሀገሮች አባ ትና የሰላም መስፍን ለመሆንም ፍላጎት ስለነበረኝ፣ እናም ትምህርትንም ለመቀ በል፣ እናም የእግዚአብሔርን ትእዛዛትን አክባሪ ለመሆን ስለፈለግሁኝ፣ [j]መብት ያለው ወራሽ፣ የአባቶችን መብት የሚይ ዘው [k]ሊቀ ካህን ሆንኩኝ።

[l]፫ ይህም ከአባቶች [m]ተሰጥቶኝ ነበር፤ ይህም ከጊዜ መጀመሪያ፣ አዎን፣ እን ዲሁም ከመጀመሪያው፣ ወይም ከምድር መመስረት በፊት እስከ አሁን ድረስ ከአ ባቶች የመጣው፣ በአባቶች በኩል ወደ እኔ የመጣው፣ እንዲሁም [n]የበኩር ልጅ፣ ወይም [o]የአዳም የመጀመሪያ ሰው፣ ወይም የመጀመሪያው አባት መብት ነበር።

[p]፬ እግዚአብሔር ስለዘር በሚመለከት ለአ ባቶች እንደመደበው የራሴን ወደ ክህነት [q]መመደብን ፈለግሁኝ።

[r]፭ [s]አባቶቼም፣ ከፅድቅና ከጌታ አም ላካቸው ከሰጣቸው ቅዱስ ትእዛዛቱ ዞር ብለው፣ የአሕዛብ አማልክትን [t]እያመ ለኩ፣ ድምጼንም ለመስማትም በፍጹም እምቢ አሉ።

[u]፮ ልባቸውም ክፉ ለማድረግ ፈቅደው ነበርና፣ እናም ወደ ኤልከናኽ [v]አምላክ፣ ሊብናኽ አምላክ፣ ማህማርከራኽ አም ላክ፣ ቆራሽ አምላክ፣ እናም ወደ ግብፅ ንጉስ ፈርዖን አምላክ በጠቅላላ ዞረዋል።

[w]፯ ስለዚህ ልጆቻቸውን ለመናገር ወደማ ይችለው ጣኦት ለመሰዋት ልቦቻቸውን ወደ አሕዛብ መስዋዕት ዞረዋል፣ እና ድምጼንም አያደምጡም፣ ነገር ግን ህይወቴን በኤል ከናኽ ቁስ ለመውሰድ ፍላጎት ነበራቸው። የኤልከናኽ ቁስ የፈርዖን ቁስም ነበር።

[x]፰ አሁን፣ በዚህ ጊዜ በከለዳውያን ሀገር ውስጥ በተሰራው መሰዊያ ድንጋይ ላይ ለእ ነዚህ ልዩ አማልክቶች ወንዶችን፣ ሴቶች

---

[a] ፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. ዑር።
ለ ቅ.መ.መ. አብርሐም።
ሐ የሐዋ. ፯፡፪–፬።
[b] ፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. ደስታ።
ለ ቅ.መ.መ. እረፍት።
ሐ ቅ.መ.መ. ጻድቅ፣ ጽድቅ።
መ ት.እና ቃ. ፵፪፡፳፩።
ቅ.መ.መ. እውቀት።
ሠ ቅ.መ.መ. የመልከ ጼዴቅ ክህነት።
ረ ቅ.መ.መ. ሊቀ ካህን።
[c] *ሀ* ት.እና ቃ. ፲፪፡፲፡።
ለ ት.እና ቃ. ፳፳፡፲፯።
ቅ.መ.መ. በኩር።
ሐ ሙሴ ፩፡፴፬።
ቅ.መ.መ. አዳም።
[d] *ሀ* ቅ.መ.መ. በኩር።
[e] *ሀ* ዘፍጥ. ፲፪፡፩።
ለ ቅ.መ.መ. ጣኦት አምላኪ።
[f] *ሀ* ይህም በመፅሐፈ አብር. ቅርፅ፣ ፩ ውስጥ በስዕል እንደሚደገፈው፣ የሀሰት አምላኮች ማለት ነው።

ንና ልጆችን መሰዋት በግብፅ ንጉስ በፈርዖን ቄስ በኩል የማቅረብ ልምድ ነበር።

፱ እንዲህም ሆነ በግብጻዊው ልምድ በኩል ቄሱ ለፈርዖው አማልክት እና ደግሞም ለሻ ግሪል አማልክት መስዋዕት አቀረበ። አሁን የሻግሪል አማልክት ጸሀይ ነበር።

፲ ኦሊሸም ሰፈር መጀመሪያ ላይ በሚገ ኘው በጲጥፋራ ተራራ ላይ ባለው መሰዊያ ላይ የፈርዖኑ ቄስ ለምስጋና ልጅን እንደመ ስዋዕት አቀረበ።

፲፩ አሁን፣ [a]ከካመን የንጉሳዊ ቤተሰብ የተወለዱትን ሶስት የኦኒታን ድንግል ሴት ልጆችን በዚህ መሰዊያ ላይ መስዋዕትን ይህም ቄስ አቀረበ። እነዚህ ደናግል እንደ መስዋዕት የቀረቡት በምግባረ መልካምነ ታቸው ምክንያት ነበር፤ እነርሱም ለእን ጨት ወይም ለድንጋይ አምላክት [b]አናመ ልክም ስላሉ፣ በመሰዊያው ድንጋይ ላይ ተገደሉ፣ እና ይህም የተደረገው የግብጻ ውያንን ስርአት በመከተል ነበር።

፲፪ እና እንዲህ ሆነ ቀሳውስትም በመሰ ዊያው ላይ ደናግሉን መስዋዕት እንዳደረ ጉት፣ እኔን ይገደሉ ዘንድ በሀይል ያዙኝ፤ እና መሰዊያው ምን አይነት እንደሆነ ታውቁ ዘንድ፣ ከዚህ መዝገብ መጀመሪያ ላይ ያለ ውን ስእል እንድትመለከቱ እመራችኋለሁ።

፲፫ በከለዳውያን ሀገር ውስጥ እንደሚሰ ራው አይነት መኝታ የሚመስል ነበር፣ እና ከኤልከናኽ፣ ሊብናኽ፣ ማህማርከራኽ፣ ቆራሽ አምላክቶች፣ ደግሞም እንደ ግብፅ ንጉስ በፈርዖን አምላክ ፊትም የቆመ ነበር።

፲፬ ስለነዚህ አማልክት ይገባችሁ ዘንድ፣ መግለጫን ከዚህ መጀመሪያ ላይ በቅርስነት ሰጥቻችኋለሁ፣ ቅርሶቹም ሃይሮግሊፊኮ ችን የሚገልጡ የከለዳውያን ራህሊኖስ አይ ነት ነበሩ።

፲፭ በመስዋዕት ህይወቴን ለማሳለፍ እጆ ቻቸውን ሲያነሱም፣ እነሆ፣ ድምጼን ወደ ጌታ አምላክ ከፍ አደረግሁኝ፣ እና ጌታም [c]አደመጠ እና ሰማ፣ እና ሁሉን በሚገ ዛው ራዕይ ሞላኝ፣ እና ከእርሱ ፊት የሚ ገኝ መልአክ በአጠገቤ ቆመ፣ እና ወዲያው እጄን [d]ፈታው።

፲፮ ድምጹም ለእኔ ነበር፥ አብርሐም፣ አብርሐም፣ እነሆ፣ ስሜ [e]ያህዌህ ነው፣ እና ሰምቼሀለሁ፣ ላድንህና ከአባትህ ቤትና ከቤተሰቦችህ ወስጄህ ወደማታውቀው እን ግዳ [f]ምድር ልወስድህ መጥቼአለሁ።

፲፯ ይህም የኤልከናኽ፣ የሊብናኽ፣ የማ ህማርከራኽ፣ የቆራሽ አምላክቶች እናም የግብፅ ንጉስ ፈርዖን አምላክን በማምለክ ልቦቻቸውን ከእኔ ዞር አድርገው ስለነበር ነው፤ ስለዚህ እነርሱን ለመጎብኘትና የአ ንተ የልጄን አብርሐምን ህይወት ለመውሰድ እጁን ያነሳውን ለማጥፋት መጥቼአለሁ።

፲፰ እነሆ፣ በእጄም እመራሀለሁ፣ እናም የእኔን ስም እንዲሁም የአባቶችህን [g]ክህ ነት በአንተ ላይ ለማድረግ እወስድሀለሁ፣ ሀይሌም በአንተ ላይ ያርፋል።

፲፱ በኖህም እንደነበረም ለአንተም ይሆ ናል፤ ነገር ግን በአንተ አልግሎት ምክንያት በኩል የእኔ [h]ስም ለዘለአለም ይታወቃል፣ እኔም የአንተ አምላክ ነኝና።

፳ እነሆ፣ የጲጥፋራ ተራራ በከላውዳው ያን ምድር [i]በዑር ከተማ ውስጥ የሚገኝ ነበር። ጌታም የኤልከናኽንና የሌሎቹን የም ድር አማልክት መሰዊያ ሰበረ፣ እና ፈጽ ሞም አጠፋቸው፣ እና ቄሱንም ገደለው፤ በከለዳውያንና በፈርዖን ቤትም ታላቅ ሀዘን ነበር፤ ፈርዖንም የንጉሳዊ ደምን የሚያመ ለክት ነበር።

፳፩ አሁን ይህ የግብፅ ንጉስም [j]ከካምን ትውልድ ዘር ነበር፣ እና በትውልድም [k]የከነዓናዊ ደም ተካፋይ ነበር።

፲፩ *a* ቅ.መ.መ. ካም።
b ዳን. ፫፡፲፫–፲፰።
፲፩ *c* ሞዛያ ፱፡፲፯–፲፰።
d አብር. ፪፡፲፫።
፲፯ *e* ቅ.መ.መ. ያህዌህ።
f ቅ.መ.መ. የቃል ኪዳን ምድር።
፲፰ *g* ቅ.መ.መ. ክህነት።
፲፱ *h* ዘፍጥ. ፲፪፡፩–፫።
፳ *i* ዘፍጥ. ፲፩፡፳፰፤ አብር. ፪፡፬።
፳፩ *j* ዘፍጥ. ፲፡፮፤ መዝ. ፷፰፡፶፩፤ ሙሴ ፯፡፲፪።
k ሙሴ ፯፡፯–፰። ቅ.መ.መ. ከነዓን፣ ከነዓናውያን።

፳፪ ከዚህም ትውልድ ግብጻውያን ሁሉ መጡ፣ በዚህም የከነዓናዊያን ደም በምድር ላይ ተጠበቀ።

፳፫ [ሀ]የግብፅ ምድርም መጀመሪያ የተገኘው በካምን ሴት ልጅ በሆነች ሴት፣ እና በከላውዴዎን ግብፅን በሚያመለክተው፣ ክልክል ማለት በሆነው በግብፅዎስ ሴት ልጅ ነበር።

፳፬ ይህን ምድር ስታገኘውም በውሃ የተዋጠ ነበር፣ ከዚያም ወንድ ልጆቿን እንዲሰፍሩበት አደረገች፤ እና እንደዚህ ከካምን እርግማኑን በምድር ላይ እንዲቀጥሉ የሚያደርጉ ዘሮች ተነሱ።

፳፭ የመጀመሪያው የግብፅ መንግስት የተመሰረተውም በካምን ሴት ልጅ ግብፅዎስ ልጅ ፈርዖን ነበር፣ እና ይህም እንደካምን መንግስት አይነት፣ ከአባት ወደ ወንድ ልጅ የሚተላለፍ፣ ነበር።

፳፮ ፈርዖንም ጻድቅ ሰው ስለነበረ፣ በህይወቱ ሁሉ በመጀመሪያ ትውልድ አባቶች እንዲሁም በመጀመሪያው ከአባት ወደ ወንድ ልጅ በሚተላለፍበት አገዛዝ፣ እንዲሁም በአዳምም አገዛዝ፣ በኩል፣ እና በምድርና በአስተዋይነት [ሀ]በረከቶች በባረከውና ክህነትን በሚመለከት በረገመው በአባቱ ኖህ የተመሰረተውንም መንግስት ስርዓት አይነት ለመመስረትም በቅንነት በመሞከር፣ መንግስቱን የመሰረተውና ህዝቡን የፈረደው በአስተዋይነትና በፍትህ ነበር።

፳፯ አሁን፣ ምንም እንኳን ፈርዖኖች ከኖህና በካነምን በኩል ይህ ይገባናል ብለው ቢዋሹምና አባቴንም ወደ ጣኦት አምልኮ ቢወስዱትም፣ ፈርዖን [ሀ]ክህነት መብት ከሌለው ወገን ነበር።

፳፰ ነገር ግን [ሀ]መዛግብቱ በእጄ ላይ ስላረፉና ከእኔም ጋር አሁንም ስላሉ፣ ከዚህ በኋላ፣ ከፍጥረት መጀመሪያ ጊዜ ጀምሮ እስከ ራሴ ድረስ ያለውን የቅድመ ተከተልን ለመዘርዘር እሞክራለሁ።

፳፱ አሁን፣ የኤልከናኽ ቄስም በመመታት ከሞተ በኋላ፣ ፅኑ ራብም በምድሩ እንደሚመጣ ከላውዴዎን በሚመለከት ለእኔ የተነገሩኝ ነገሮችም በሙሉ እየተሟሉ መጡ።

፴ እንደዚህም ፅኑ ራብም በከላውዴዎ ሀገር በሙሉ ገባ፣ እና አባቴም በረሀብ ምክንያት በጣም ተሰቃየ፣ እና እኔ ላይ ክፉ ነገር እንዲመጣ፣ ህይወቴን [ሀ]ለመውሰድ፣ ላደረጋቸው ጥፋትም ንስሀ ገባ።

፴፩ ነገር ግን የአባቶችን፣ እንዲሁም የፔትርያርኮቹን፣ የክህነት መብትን የሚመለከቱ መዛግብትን ግን ጌታ አምላኬ በእጆቼ ጠበቃቸው፤ ስለዚህ የፍጥረት መጀመሪያ እውቀቶች፣ እና ደግሞም [ሀ]የአለማትና የከዋክብት እውቀቶችም ለአባቶች እንደተገለጹላቸው፣ እኔም እስከዚህ ቀን ድረስ ጠብቄአለሁ፣ እና አንዳንድ እነዚህን ነገሮች በዚህ መዝገብ ላይ ከእኔ በኋላ ለሚመጡት ትውልዶች ጥቅም ለመጻፍ እሞክራለሁ።

ምዕራፍ ፪

አብርሐም ከዑር ወጥቶ ወደ ከነዓን ሄደ—ሀራን ውስጥም ያህዌህ ተገለጠለት—የወንጌል በረከቶችም ሁሉ ለዘሮቹና በዘሩም በኩል ለሁሉም ቃል ተገብተዋል—ወደ ከነዓንና ወደ ግብፅ ሄደ።

፩ አሁን በዑር ውስጥ ጌታ አምላክ ረሀቡ በጣም ፅኑ እንዲሆን አደረገ፣ በዚህም ምክንያት ወንድሜ [ሀ]ሀራንም ሞተ፤ አባቴ [ለ]ታራን ግን በከለዳ ሃገር ዑር ውስጥ መኖር ቀጠለ።

፪ እና እንዲህ ሆነ እኔ አብርሐም [ሀ]ሦራን አገባሁ፣ እናም ወንድሜ [ለ]ናኮር የሃራን ሴት ልጅ ሚልካን አገባ።

፳፫ ሀ ቅ.መ.መ. ግብፅ።
፳፮ ሀ ቅ.መ.መ. መባረክ፣ የተባረከ፣ በረከት።
፳፯ ሀ አ.አ. ፪።
ቅ.መ.መ. ክህነት።
፳፰ ሀ ሙሴ ፮፥፭።
ቅ.መ.መ. የመታሰቢያ መፅሐፍ።
፴ ሀ አብር. ፩፥፯።
፴፩ ሀ አብር. ፫፥፩–፲፰።
፪ ፩ ሀ ዘፍጥ. ፲፩፥፳፰።
ለ ዘፍጥ. ፲፩፥፳፬–፳፮፤ ፩ ዜና ፩፥፳፮።
፪ ሀ ዘፍጥ. ፲፩፥፳፱።
ቅ.መ.መ. ሳራ።
ለ ዘፍጥ. ፲፩፥፳፯፤ ፳፪፥፳–፳፬።

፫ አሁን ጌታ እንዲህ [ሀ]አለኝ፥ ከአገርህ
ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ
እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ።

፬ ስለዚህ ወደ ከነዓን ምድር ለመሄድ የከ
ለዳውያን [ሀ]ዑር ምድር ትቼ ሄድኩኝ፤ እና
የወንድሜን ልጅ ሎጥንና ሚስቱን እናም
ሚስቴን ሦራን ይዤ ሄድኩኝ፤ እና [ለ]አባ
ቴም ሃራን ብለን ወደጠራነው ምድርም
ተከተለኝ።

፭ ረሀቡም ቀነሰ፤ እናም ብዙ መንጋዎች
በሀራን ስለነበሩ አባቴም በዚያ ቆየ፤ እና
አባቴ [ሀ]ጣኦቶችን ወደማምለክ ተመለሰ፣
ስለዚህ በሀራን ውስጥ መኖር ቀጠለ።

፮ ነገር ግን እኔ አብርሐምና የወንድሜ
ልጅ [ሀ]ሎጥ ወደ ጌታ ጸለይን፣ እና ጌታም
ለእኔ [ለ]ተገልጦ እንዲህ አለኝ፥ ተነሳ፣ እና
ሎጥን ከአንተ ጋር ውሰድ፤ አንተን ከሄራን
ለማውጣት እና ለዘርህ፣ ድምጼን ሲያደ
ምጡ፣ ለዘለአለም እንዲወስዱ ለምሰጠው
እንግዳ [ሐ]ምድር ውስጥ [መ]ስሜን የምትሸ
ከም አገልጋይ አደርግህ ዘንድ እንድትሄድ
አላማ አለኝ።

፯ እኔ ጌታ አምላክ ነኝና፤ በሰማይም እኖ
ራለሁ፤ ምድርም የእግሬ [ሀ]ማረፊያ ነች፤
እጄን በባህር ላይ እዘረጋለሁ፣ እና በድ
ምጼም ይታዘዛል፤ ንፋሱን እሰራለሁ እና
እሳትን [ለ]ሰረገላዬ አድርጌአለሁ፤ ለተራ
ሮች—ከዚህ ሂዱ—እላለሁ እና እነሆ፣
በታላቅ አውሎንፋስ ወዲያውም ይወሰ
ዳሉ።

፰ ስሜ [ሀ]ያህዌህ ነው፣ እና መጨረሻ
ውን ከመጀመሪያው [ለ]አውቀዋለሁ፤ ስለ
ዚህ እጄም በአንተ ላይ ይሆናል።

፱ ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ፣ እና አብ
ዝቼም [ሀ]እባርክሀለሁ፣ እና ስምህንም ከህዝ
ቦች መካከል ታላቅ አደርገዋለሁ፣ እና ከአ
ንተ በኋላ ለሚመጡ ዘሮች በረከት ሆነህ፣
እጆቻቸው ይህን አገልግሎትና [ለ]ክህነትን
ለሁሉም ህዝቦች ይዘው ይሄዳሉ፤

፲ እና በስምህ በኩልም እባርካቸዋለሁ፤
ይህን [ሀ]ወንጌል የተቀበሉት ሁሉ በአንተ
ስም ይጠራሉ፣ እና እንደ አንተ [ለ]ዘር ይቆ
ጠራሉ፣ እና እንደ [ሐ]አባታቸው ተነስተው
ይባርኩሀል፤

፲፩ የሚባርኩህንም [ሀ]እባርካለሁ፣ የሚረ
ግሙህንም እረግማለሁ፤ በአንተ (ይህም
ማለት በክህነትህ በኩል) እናም [ለ]በዘርህ
(ይህም ማለት በክህነትህ)፣ እና ከአን
ተም በኋላ በዘርህ (ይህም ማለት የራስህ
ዘር ወይም የሰውነትህ ፍሬዎች) በኩል ይህ
[ሐ]መብት ይቀጥላል፣ ሁሉም የምድር ቤተ
ሰቦች በደህንነት በረከቶች፣ እንዲሁም የዘ
ለአለም ህይወት በሆኑት የወንጌል በረከ
ቶች ይባረካሉ ብዬ ቃል ኪዳን ሰጥቼሀለሁ።

፲፪ አሁን ጌታ ከእኔ ጋር መናገሩን ከጨ
ረሰ በኋላና ፊቱንም ከእኔ ከወሰደም በኋላ፣
በልቤ እንዲህ አልኩ፥ አገልጋይህ በትኩ
ረት [ሀ]ፈልጎህ ነበር፤ አሁን አገኘሁህ፤

፲፫ ከኤልከናኽ አማልክቶችም እኔን
[ሀ]ለማዳን መላእክትህን ላክ፣ እና ድምፅ

፫ ሀ ዘፍጥ. ፲፪፥፩፤
የሐዋ. ፯፥፩–፫።
፬ ሀ ነህ. ፱፥፯።
ለ ዘፍጥ. ፲፩፥፴፩–፴፪።
፭ ሀ ኢያ. ፳፬፥፪።
፮ ሀ ቅ.መ.መ. ሎጥ።
ለ ዘፍጥ. ፲፯፥፩።
ቅ.መ.መ. ኢየሱስ
ክርስቶስ—የክርስቶስ
ቅድመ ምድራዊ ህይወት።
ሐ ዘፍጥ. ፲፫፥፲፬–፲፭፤ ፲፯፥፰፤
ዘፀአ. ፴፫፥፩።
ቅ.መ.መ. የቃል
ኪዳን ምድር።
መ ዘፍጥ. ፲፪፥፪–፫፤
አብር. ፩፥፲፱።
፯ ሀ ፩ ኔፊ ፲፯፥፴፱፤
ት. እና ቃ. ፴፰፥፲፯።
ለ ኢሳ. ፷፮፥፲፭–፲፮።
፰ ሀ ቅ.መ.መ. ያህዌህ።
ለ ቅ.መ.መ. ሁሉን የሚያውቅ።
፱ ሀ ፩ ኔፊ ፲፯፥፵፤
፪ ኔፊ ፳፱፥፲፬፤
፫ ኔፊ ፳፥፳፯፤
ሞር. ፭፥፳።
ቅ.መ.መ. አብርሐም—
የአብርሐም ዘር።
ለ ት. እና ቃ. ፹፬፥፲፯–፲፱፤
ሙሴ ፮፥፯።
ቅ.መ.መ. የመልከ
ጼዴቅ ክህነት።
፲ ሀ ገላ. ፫፥፯–፱።
ለ ዘፍጥ. ፲፫፥፲፮፤
ገላ. ፫፥፳፱፤
፪ ኔፊ ፴፥፪።
ሐ ቅ.መ.መ. የአባቶች
አለቃ፣ ፓትሪያርክ።
፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. የአብርሐም
ቃል ኪዳን።
ለ ኢሳ. ፷፩፥፱።
ሐ ቅ.መ.መ. በኩር፤
እስራኤል፤
ክህነት።
፲፪ ሀ ት. እና ቃ. ፹፰፥፷፫።
፲፫ ሀ አብር. ፩፥፲፭–፲፯።

ህን ባደምጥ ለእኔ ጥቅም ይሆናል፣ ስለ ዚህ አሁን ባሪያህም ይነሳ እና በሰላም አሰ ናብተው።

፲፬ ስለዚህ እኔ አብርሐም ጌታ እንዳለኝ ተነስቼ ሄድኩ፣ ሎጥም ከእኔ ጋር፤ እና እኔ አብርሐምም ከካራን ስሄድ ᵐስልሳ ሁለት አመቴ ነበር።

፲፭ እና በከላውዴዎ ᵐበዑር ውስጥ እያ ለሁ ያገባኋት ᵃሦራን እና የወንድሜ ልጅ ሎጥን፣ እና የሰበሰብናቸውን ነገሮች፣ እና በካራን ውስጥ ʰያገኘናቸውን ነፍሳት ወሰ ድኩ፣ እና ወደ ᵐከነዓንም ምድር ገባን፣ እና ስንጓዝም በድንኳን ውስጥ ኖርን፤

፲፮ ስለዚህ፣ ከካራን ተጉዘን በጀርሸን በኩል ወደ ከነዓን ምድር ስንመጣም፣ ዘለ አለምዊውም ከለላችን ᵐአለታችንና መድ ሀኒታችን ነበር።

፲፯ አሁን እኔ አብርሐም ᵐመሰዊያ በጀ ርሸን ምድር ውስጥ ሰራሁ፣ እና ለጌታም መስዋዕትን አቀረብኩ፣ እና እንዳይሞቱም ከአባቴ ቤት ᵃረሀቡ ጋብ እንዲል ጸለይኩ።

፲፰ ከዚያም እስከ ሴኬም ድረስ ከጀ ርሸን ምድሪቱ ዘልቀን አልፈን ሄድን፤ ይህም በሞሬ ሜዳ ውስጥ የነበረ ነው፣ እና ᵐበከነዓናውያን ድንበርም ደርሰን ነበር፣ እናም በባእድ አምላኪዎች ምድር ውስጥ ስለገባን፣ በሞሬ ሜዳ አካባቢም ᵃመስዋዕ ትን አቀረብኩ፣ ጌታንም በመንፈሳዊ ነገር ተግቼ ጠራሁት።

፲፱ እናም ጌታ ጸሎቴን ለመመለስ ተገ ለጠልኝ፣ እና እንዲህም አለኝ፥ ይህችን ᵐምድር ለዘርህ እሰጣለሁ።

፳ እና እኔ አብርሐም ለጌታ ከሰራሁት መሰዊያ ተነሳሁ፣ ᵐበቤቴል ምሥራቅ ወዳ ለው ተራራም ሄድኩ፣ እና ቤቴልን በም ዕራብ፣ ᵃጋይን በምስራቅ ሆኖ ድንኳኔን በዚያ ተከልኩ፤ እና በዚያም ለጌታ ሌላ መሰዊያን ሰራሁ፣ እና ደግሜም የጌታን ስም ʰጠራሁ።

፳፩ እና እኔ አብርሐም ወደ ደቡብ መጓ ዝን ቀጠልኩ፤ በዚያም ምድር ውስጥ ረሀብ ይበረታ ነበር፤ እና እኔ አብርሐም ረሀቡ ፅኑ ስለነበር፣ ወደ ግብፅ ለመሄድ፣ እና ወደዚ ያም ለመጓዝ ወሰንኩ።

፳፪ ግብፅ ለመግባት እየቀረብኩ ስመ ጣም፣ ጌታም እንዲህ አለኝ፥ እነሆ፣ ሚስ ትህ ᵐሦራ ለመመልከት መልከ መልካም ሴት ነች፤

፳፫ ስለዚህ እንዲህ ሆነ ግብጻውያን እር ሷን በሚያዩበት ጊዜ ይህች ሚስቱ ናት ይላሉ፤ እና ይገድሉሀል፣ እርሷን ግን በህ ይወት ይተውአታል፤ ስለዚህ እንዲህ አድ ርግ።

፳፬ ለግብጻውያኑ እህትህ እንደሆነች ትን ገራቸው፣ ነፍስህም ትድናለች።

፳፭ እንዲህም ሆነ እኔ አብርሐም ጌታ የነገረኝን ሁሉ ለሚስቴ ሦራ ነገርኋት—ለአንቺም ደህንነት፣ እና በአንቺም ምክን ያት ነፍሴ ትድን ዘንድ፣ በአንቺ ምክንያት መልካም ይሆንልኝ ዘንድ እንግዲህ እህቴ እንደሆንሽ እንድትነግሪያቸው እለምንሻ ለሁ።

ምዕራፍ ፫

አብርሐም ስለጸሀይ ጨረቃና ከዋክብት በኡሪምና ቱሚሙን መሰረት ተማረ—ስለመንፈሶች ዘለአለማዊነት ጌታ ገለጠ ለት—ከምድር በፊት ስለነበረው ህይወት፣ ስለቀድሞ መመረጥ፣ ስለፍጥረት፣ ስለአ ዳኝ ምርጫ፣ እና ስለሰው ዳግመኛ ሁኔታ ተማረ።

፲፩ *ሀ* ዘፍጥ. ፲፪፡፩–፭።
፲፭ *ሀ* ቅ.መ.መ. ዑር።
ለ ቅ.መ.መ. ሳራ።
ሐ ቅ.መ.መ. መቀየር፣ የተቀየረ።
መ ቅ.መ.መ. ከነዓን፣ ከነዓናውያን።
፲፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. አለት።
፲፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. መሰዊያ።
ለ አብር. ፩፡፳፱።
፲፰ *ሀ* ዘፍጥ. ፲፪፡፮።
ለ ቅ.መ.መ. መስዋዕት።
፲፱ *ሀ* ዘፍጥ. ፲፫፡፲፪–፲፭፤ ፲፯፡፳፤ ዘፀአ. ፫፡፩–፲፣ ዘኁል. ፴፬፡፪። ቅ.መ.መ. የቃል ኪዳን ምድር።
፳ *ሀ* ቅ.መ.መ. ቤቴል።
ለ ዘፍጥ. ፲፫፡፫–፬።
ሐ ዘፍጥ. ፲፪፡፳።
፳፪ *ሀ* ዘፍጥ. ፲፪፡፲፩–፲፫።

፩ እና እኔ አብርሐም በከለዳውያን ዑር ውስጥ ጌታ አምላኬ የሰጠኝ ᵐኡሪምና ቱሚም ነበረኝ፣

፪ እና ᵐከዋክብቱ ታላቅ እንደነበሩ፣ እና አንድያውም በእግዚአብሔር ዙፋን አጠገብ ቀርቦ ይገኝ እንደነበር አየሁ፤ እና በአጠገቡም የነበሩ ብዙ ታላላቆችም ነበሩ፤

፫ እና ጌታም እንዲህ አለኝ፥ እነዚህ ገዢዎች ናቸው፤ እና አጠገቤ ስለሆነና፣ የታላቁ ስም ᵐቆሎብ ነው፣ እኔ ጌታ አምላክ ነኝና፥ ይህ ከቆምክበት አንድ አይነት ስርዓት ለሆኑት ሁሉ እንዲመራም ሰጥቼዋለሁ።

፬ በኡሪምና ቱሚም እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ፥ ያ ቆሎብ በሚዞርበት ጊዜያትና ወቅቶች መሰረት፣ እንደ ጌታ ስርዓት አማካይነት ነው፤ እናም አምላክ እንደሚያውቀው የአንድ ᵐቀን መዞሪያ፣ አንተ በቆምክበት ስፍራ እንደተሰጠው ሰአት አንድ ሺህ ᶮአመት ነው። ይህም በቆሎብ የሚቆጠረው ሰአት፣ አምላክ የሚቆጥርበት ሰአት ነው።

፭ ጌታም እንዲህ አለኝ፥ ታናሽ ብርሃን ያላት አለም፣ ቀኑን ከምታሰለጥነው በታች ብርሃን ያላት፣ እንዲሁም የማታው፣ አንተ አውቀሀት ከምትቆምባት አለም በላይ ታላቅ ነች፣ ይህች የምትሄደው በዝግታ ስለሆነ ነውና፤ ይህም ስርዓቱ የሆነበት ምክንያት ከቆምክበት መሬት በላይ ስለሚገኝ ነው፣ ስለዚህ የሚቆጠርበት ሰአቱ ከቀናት፣ ወራትና አመታት ቁጥር አይነት የሚበዛ አይደለም።

፮ ጌታም እንዲህ አለኝ፥ አሁን፣ አብርሐም፣ እነዚህ ᵐሁለት እውነቶች አሉ፣ እነሆ አይኖችህ ይህን አይተዋል፤ አንተም የጊዜ አቆጣጠርን፣ እና ሰአትን እንድትወስን፣ አዎን፣ በቆምክበት ምድር ላይ ሰአትን ለመወሰን፣ እና ቀኑን እንድታሰለጥን ለተሰጣት ብርሀን ሰአትን ለመወሰን፣ እናም ማታውንም እንድትመራ ለተሰጣት ታናሽ ብርሀን ሰአትን ለመወሰን ስለተሰጣት እንድታውቅ ተሰጥቶሀል።

፯ አሁን ለታናሿ ብርሀን የተወሰነው ሰአት አንተ ከቆምክበት ምድር ከሚቆጠረው ጊዜ በላይ በጣም ረጅም ነው።

፰ እና እነዚህ ሁለት እውነቶች በሚገኙበት፣ ሌላ የሚበልጣቸው እውነትም ይገኛል፣ ይህም የጊዜ አቆጣጠሩ ከዚህ የሚበልጥ ሌላ አለምም አለ።

፱ እንደዚህም በጌታ ጊዜ አቆጣጠር ከሆነው ወደ ቆሎብ እስክትመጣ ድረስ፣ ከአንዱ አለም ውስጥ በአቆጣጠር ከሌላው የሚበልጥ አለ፤ ቆሎብም በእግዚአብሔር ዙፋን አጠገብ፣ አንተ በቆምክበት ስፍራ አይነት ᵐስርዓት ካላቸው ሌሎች አለማትን እንድትመራ የተወሰነች ነች።

፲ እና ወደ እግዚአብሔር ዙፋን እስክት ቀርብ ድረስ፣ ብርሀን እንዲሰጡ ለታዘዙት ከዋክብት ላይ እንዴት ጊዜ እንደሚቆጠሩ እንድታውቅ ተሰጥቶሀል።

፲፩ እንደዚህም እኔ አብርሐም ከጌታ ጋር ፊት ለፊት፣ አንድ ሰው ከሌላ ጋር እንደ ሚነጋገር ᵐተነጋገርኩ፤ እና በእጁም ስለሰራቸው ስራዎችም ነገረኝ፤

፲፪ እና እንዲህም አለኝ፥ ልጄ ሆይ ልጄ ሆይ (እና እጁ ተዘርግቶ ነበር)፣ እነሆ እነዚህን ሁሉ ነገሮች አሳይሀለሁ። እና እጁን በአይኖቼ ላይ አደረገ፣ እና በእጁ የሰራቸውን እነዚያን ነገሮች አየሁ፣ እነርሱም ብዙ ነበሩ፤ እና በአይኔ ፊት ተባዙ፣ እና መጨረሻቸውንም ማየት አልቻልኩም።

፲፫ እና እንዲህም አለኝ፥ ይህ ሽኒህህ፣ ይህም ጸሀይ ነው። እና እንዲህም አለኝ፥ ቆቆብ፣ ይህም ኮኮብ ነው። እና እንዲህም አለኝ፥ ኦሌያ፣ ይህም ጨረቃ ነው። እና እንዲህ አለኝ፥ ቆቃውቢም፣ ይህም ከዋ

፲ ፩ *ሀ* ዘፀአ. ፳፰፡፴፣ ፴፣ ሞዛያ ፳፡፲፫፣ ፳፰፡፲፫–፲፯፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፴፭። ቅ.መ.መ. ኡሪም እና ቱሚም።

፪ *ሀ* አብር. ፩፡፴፭።

፫ *ሀ* አብር. ቅርፅ ፪፣ ስዕል ፩–፳ ተመልከቱ። ቅ.መ.መ. ቆሎብ።

፬ *ሀ* አብር. ፭፡፲፫።

ለ መዝ. ፺፡፬፣ ፪ ጴጥ. ፣፡፳።

፭ *ሀ* አብር. ፣፡፲–፲፱።

፱ *ሀ* ት. እና ታ. ፹፳፡፴፱–፵፩።

፲፩ *ሀ* ዘፍጥ. ፲፯፡፩፣ ዘጉል. ፲፪፡፭–፳።

፲፪ *ሀ* ዘፍጥ. ፲፯፡፲–፲፱።

ክብት ማለት፣ ወይም በሰማይ ጠፈር ላይ የሚገኙት የነበሩ ሁሉም ታላቅ ብርሃናት ናቸው።

፲፬ እና እነዚህን ቃላት ጌታ ሲነግረኝ ምሽት ነበር፥ አንተን እና ከአንተ በኋላ የሚመጡትን ዘሮችህን ᵐአበዛለሁ፤ እና አሸዋዎችን ᵃመቁጠር ከቻልክ፣ የአንተ ᵐዘር ቁጥርም እንዲሁ ይሆናል።

፲፭ አምላክም እንዲህ አለኝ፥ አብር ሐም፣ እነዚህን ቃላትን ትገልጽ፣ ወደግ ብፅ ከመግባትህ በፊት እነዚህን ነገሮች አሳ የሁህ።

፲፮ ሁለት ነገሮች ቢኖሩ፣ እና አንዱም ከሌላው በላይ ቢሆን፣ ከእነርሱም በላይ የሚበልጡም ነገሮች ይኖራሉ፤ ስለዚህ ᵐቆሎብ ካየሀቸው ቆቃውቢም በላይ ሁሉ ታላቅ ነው፣ ምክንያቱም ይህም ከሁሉም በላይ የቀረበ ስለሆነ ነው።

፲፯ አሁን፣ ሁለት ነገሮች ቢኖሩ፣ አን ዱም ከሌላው በላይ ቢሆን፣ እና ጨረቃም ከምድር በላይ ብትሆን፣ ከዚያም ከዚህም በላይ የሆነ ሌላ አለም ወይም ኮኮብ ይኖ ራል፤ እና ጌታ አምላክህ ᵐለሚያደርጋቸው ነገሮች ካልሆነ በስተቀር በልቡ ለማድረግ የሚያስብ ምንም ነገር የለም።

፲፰ ታላቅ ኮኮብ እንዴት ሰራ፤ ደግሞም፣ ሁለት መንፈሶች ከኖሩ፣ እናም አንዱ ከሌ ላው በላይ ባለእውቀት ከሆነ፣ ምንም እን ኳን አንደኛው ከሌላው ባለእውቀት ቢሆ ንም እነዚህ መንፈሶች መጀመሪያ የላቸ ውም፤ ከዚህ በፊትም ኖረዋል፣ መጨረ ሻም አይኖራቸውም፣ ከዚህ በኋላም ይኖ ራሉ፣ እነርሱ ᵐግኖሉም፣ ወይም ዘለአለ ማዊ ናቸውና።

፲፱ ጌታም እንዲህ አለኝ፥ እነዚህ ሁለት እውነቶች አሉ፣ ሁለት መንፈሶች አሉ፣ እናም አንዱ ከሌላው በላይ እውቀተኛ ነው፤ ከእነርሱ በላይ እውቀት ያለው ሌላም ይኖራል፤ እኔ ጌታ አምላክህ ነኝ፣ እኔም ᵐከሁሉም በላይ እውቀተኛ ነኝ።

፳ ጌታ አምላክህ መላእክቱን ሰዶ ከኤል ከናኽ ቄስ እጆች ᵐአድኖሀል።

፳፩ ከእነርሱ ሁሉ መካከል እኖራለሁ፤ ስለዚህ አሁን ወደ አንተ ዘንድ፣ ከሁሉም ውስጥ ጥበቤ ታላቅ በሆነው፣ በእጄ ስለተ ሰሩት ᵐስራዎች ልገልፅልህ ወርጄአለሁ፣ አይኖችህ ከመጀመሪያ ጊዜ ጀምሮ ካዩ ዋቸው ባለእውቀቶች ሁሉ ላይ ᵃበጥበብና በጥንቃቄ በበላይ ሰማይንና በበታች ምድ ርን እመራለሁና፤ ካየሀቸውም ባለእውቀ ቶች መካከል በመጀመሪያም ወርጄአለሁ።

፳፪ አሁን ለእኔ አብርሐም ጌታ አለም ከመመስረቱ ᵐበፊት የነበሩትን ᵃባለእው ቀቶችን አሳየኝ፤ ከእነዚህ መካከልም ብዙ ታላቅ እና ᵐመኳንንትም ነበሩ።

፳፫ እና እግዚአብሔር እነዚህ ነፍሶች መልካም እንደሆኑ አየ፣ እና በመካከላቸ ውም ቆመ፣ እንዲህም አለ፥ እነዚህን መሪ ዎቼ አደርጋለሁ፤ መንፈስ ከሆኑት መካ ከል ቆሞ ነበርና፣ እና መልካምም እንደነበሩ አየ፤ እንዲህም አለኝ፥ አብርሐም፣ አንተ ከእነርሱ አንዱ ነህ፤ ከመወለድህ በፊትም ᵐተመርጠህ ነበር።

፳፬ እና ከእነርሱም መካከል እግዚአብ ሔርን የሚመስል ᵐአንድም ቆሞ ነበር፣ እና ከእርሱ ጋር ለነበሩትም እንዲህ አላቸው፥ እንወርዳለን፣ በዚያም ስፍራ አለና፣ እና እነዚህን ነገሮች እንወስዳለን፣ እና እነዚህ

፲፬ ሀ አብር. ፪፡፱።
ለ ዘፍጥ. ፳፪፡፲፯፣ ሆሴ. ፩፡፲።
ሐ ዘፍጥ. ፲፫፡፲፯፣ ት. እና ቃ. ፮፴፪፡፴።
፲፯ ሀ አብር. ፫፡፫።
፲፯ ለ ኢዮብ ፱፡፭–፲፪።
፲፰ ሀ ግኖሉም ዘለአለም የሚል ትርጉም ያለው የዕብራውያን ቃል በዕብራውያን አባባል የተጻፈበት ነው።
፲፱ ሀ ኢሳ. ፶፭፡፰–፱። ቅ.መ.መ. ሁሉን የሚያውቅ።
፳ ሀ አብር. ፩፡፲፭።
፳፩ ሀ ት. እና ቃ. ፲፰፡፴–፴፯፣ ሙሴ ፩፡፳፯–፳፱።
ለ ቅ.መ.መ. ጥበብ።
፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. ቅድመ ምድራዊ ህይወት፣ የሰማይ ሽንጎ።
ለ ቅ.መ.መ. እውቀተኛነት፣ እውቀተኛዎች።
ሐ ት. እና ቃ. ፮፴፰፡፶፭።
፳፫ ሀ ኢሳ. ፵፱፡፩–፭፣ ኤር. ፩፡፭። ቅ.መ.መ. መምረጥ፣ መረጠ፣ የተመረጠ (ግስ)፤ ቀድሞ መመረጥ።
፳፬ ሀ ቅ.መ.መ. በኩር።

ከመፅሐፈ አብርሐም ቅርፅ

ቁጥር ፪



መግለጫ

ስዕል ፩ ይህ የመጀመሪያውን ፍጥረትና ከሰለስቲያል ወይም ከእግዚአብሔር መኖሪያ አጠገብ ያለው ቆሎብ ነው። የመጀመሪያው በመንግስት ውስጥ፣ የመጨረሻውም ከሰአት መለኪያ ጋር ግንኙነት ያለው ነው። በሰለስቲያል ሰአትም አንድ ቀንን ከክንድ ጋር ያመዛዝናቸው፣ በሰለስቲያል ጊዜ መሰረት መለኪያ። አንድ ቀን በቆሎብ በዚህ አለም አቆጣጠር መሰረት፣ በግብጻውያን ጃሆህኽ እንደሚባለው፣ አንድ ሺህ አመታት ጋር እኩል ነው።

ስዕል ፪ ለጌታ በሰራው በመሰዊያ ላይ መስዋዕት ሲያደርግ ለአብርሐም ከእግዚአብሔር የተገለጠለት፣ በግብጻውያን ኦሊብሊሽ ተብሎ የሚጠራው፣ በሰለስቲያል ወይም እግዚአብሔር በሚኖርበት ስፍራ አጠገብ የሚገኘው የሚቀጥለው ታላቅ ፍጥረት፤ ከሌሎች አለማት ጋር በመገናኘት፣ ደግሞም የሀይል ቁልፍን የያዘ።

ስዕል ፫ የዘለአለማዊ ብርሃን ዘውድ በራሱ ላይም ተደርጎ፣ እግዚአብሔር በሀይልና በስልጣን ተሸፍኖ በዙፋን ላይ ተቀምጦ ለማሳየት ነው፤ በዔድን ገነት ውስጥ ለአዳም፣ ደግሞም ለሴት፣ ለኖህ፣ ለመልከ ጼዴቅ፣ ለአብርሐም ክህነት ተገልጦላቸው ለነበሩት ሁሉ የተገለጠውን የቅዱሱ ክህነት ታላቁ ቁልፍ ቃላትን የሚወክል ነው።

ስዕል ፬ ጠፈርን፣ ወይም የሰማያት ጠፈርን በማስመልከት ራኡኪያንግ ለእብራውያን ቃል መልስ የሚሰጥ፤ ደግሞም በግብጻዊ አንድ ሺ የሚል ቁጥር ስዕል፤ በቆሎብ መዞሪያና ከሰአት መለኪያ ጋር አንድ የሆነው፣ ኦሊብሊሽ ለሚባለው ሰአት መለኪያ መልስ የሚሰጥ ነው።

ስዕል ፭ በግብጻዊ ቋንቋ እኒሽ-ጎ-ኦን-ዶሽ ተብሎ ይጠራል፤ ይህ ደግሞም ከመሪ አለማት አንዱ ነው፣ በግብጻውያን ጸሀይ፣ እና ከቆሎብ ታላቅ ቁልፍ በሆነው ወይም በሌላ ቃላትም አስራ አምስት ሌሎች የማይነቃነቁ አለማትን ወይም ከዋክብትን፣ ደግሞም እንደ ፍሎኢስ ወይም ጨረቃ፣ ምድርና ጸሃይን በአመታዊ መዘዋወራቸው የሚመራ ገዢ ሀይል በኬ-ር-ቫንራሽ በኩል ብርሃኑን የሚዋስ ነው። ይህ አለም ሃይሉን የሚያገኘው በክሊ-ፎሎስ-ኢስ-እስ፣ ወይም በሀ-ኮ-ኮ-ቢም በኩል ነው፣ በቁጥር ሀያ ሁለትና ሀያ ሶስት የሚወከሉት ከዋክብት ብርሃንን የሚቀበሉት በቆሎብ መዘዋወሪያዎች ነው።

ስዕል ፮ ይህም ምድርን በአራት የምድር መዓዘናት ይወክላል።

ስዕል ፯ እግዚአብሔር በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ፣ በሰማይ የክህነት ታላቅ ቁልፍ-ቃላት በኩል መገለጥን ይወክላል፤ ደግሞም፣ በርግብ አምሳል ለአብርሐም የተሰጠው የመንፈስ ቅዱስ ምልክት።

ስዕል ፰ ለአለም ሊገለጽ የማይቻል ጽህፈት ያለበት፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ቅዱስ ቤተመቅደስ የሚገኝ ነው።

ስዕል ፱ በዚህ ጊዜ መገለጥ የለበትም።

ስዕል ፲ ይህኛውም።

ስዕል ፲፩ ይህኛውም። አለም እነዚህ ቁጥሮችን ለማግኘት ከቻሉ፣ እንዲህም ይሁን። አሜን።

ሰእሎች ፲፪፣ ፲፫፣ ፲፬፣ ፲፭፣ ፲፮፣ ፲፯፣ ፲፰፣ ፲፱፣ ፳፣ ፳፩ እግዚአብሔር በፈቀደ ጊዜ ይሰጣሉ።

ከዚህ በላይ ያሉትን ትርጉሞች በዚህ ጊዜ ለመስጠት ባለን መብት ነው የሰጠነው።

ሊኖሩበት የሚችሉበትን ^ምድርን ሓእን ሰራለን፤

፳፭ እና ጌታ አምላክ የሚያዛቸውን ማና ቸውንም ነገሮች ሁሉ ^ሀእንደሚያደርጉ ለማየት፣ በዚህ ^ እንፈትናቸዋለን፤

፳፮ እና ^የመጀመሪያ ሁኔታቸውን የጠበ ቁትም ይጨመርላቸዋል፤ እና ይህን የመ ጀመሪያውን ሁኔታቸውን ያልጠበቁትም ከዚህ አይነት መንግስት ውስጥ የመጀመ ሪያው ሁኔታቸውን ከጠበቁት ጋር ክብር አይኖራቸውም፤ እና ^ሁለተኛ ሁኔታቸውን የጠበቁትም በራሳቸው ላይ ሓክብር ከዘለ አለም እስከ ዘለአለም ይጨመርላቸዋል።

፳፯ እና ^ጌታ እንዲህ አለ፥ ማንን እልካ ለሁ? እና አንዱም እንደ ^ሰው ልጅ መለሰ፥ እዚህ አለሁ፣ እኔን ላከኝ። እና ሓሌላም መለሰ እና እንዲህም አለ፥ በዚህ አለሁ፣ እኔን ላከኝ። እና ጌታ እንዲህ አለ፥ የመ ጀመሪያውን እልካለሁ።

፳፰ እና ^ሁለተኛውም ተቆጣ፣ እና የመ ጀመሪያ ሁኔታውን አልጠበቀም፤ እናም በዚያም ቀን፣ ^ብዙዎች ተከተሉት።

ምዕራፍ ፱

አማልክት ምድርንና በዚያም ህይወቶችን በሙሉ ለመፍጠር አቀዱ—በስድስት ቀን የመፍጠሪያ እቅዳቸው ተዘርዝረዋል።

፩ እና ጌታም እንዲህ አለ፥ ወደዚያ እን ውረድ። ^በመጀመሪያውም ጊዜ ወረዱ፣ እና እነርሱ፣ ይህም ማለት አማልክቱ፣ ወረዱና ሰማያትንና ምድርን ^መሰረቱም ሰሩም።

፪ ከምድር ሌላ ምንም ነገሮች ስላልሰሩ፣ ምድርን ከሰሯት በኋላ ባዶ እና ባዶማ ነበ ረች፤ ጭለማም በጥልቁ ፊት ላይ ነግሶ ነበር፣ እናም የአማልክቱ መንፈስም በው ሃዎቹ ፊት ላይ በቅርበት ^ተንጠለጠሉ።

፫ እነርሱም (አማልክቱ) ብርሀን ይሁን አሉ፤ እና ብርሃንም ሆነ።

፬ እና እነርሱ (አማልክቱ) ብርሀኑ ገባ ቸው፣ ደማቅ ነበርና፤ እና እነርሱም ብር ሀኑን ከጭለማ ከፋፈሉት፣ ወይም እንዲከ ፋፈል አደረጉት።

፭ አማልክቱም ብርሀኑን ቀን ብለው ጠሩት፣ እና ጭለማውን ሌሊት ብለው ጠሩት። እንዲህም ሆነ ከምሽት እስከ ጠዋት ድረስ ሌሊት ብለው ጠሩት፤ ከጠዋት እስከ ምሽት ድረስም ቀን ብለው ጠሩት፤ እና ቀንና ሌሊት ብለው ከጠሩት ይህ የመጀ መሪያው ቀን ነበር።

፮ አማልክቱም ደግመው እንዲህ አሉ፥ በውሃዎቹ መሀከል ^ጠፈር ይኑሩ፣ እና ይህም ውሀዎችን ከውሀዎች ይክፈል።

፯ እና አማልክቱ ጠፈሩን አዘዙ፣ በዚህም ይህም ከጠፈሩ በታች የነበሩትን ከጠፈሩ በላይ ከነበሩት ከፋፈላቸው፤ እና እንደዚ ህም፣ እንዲሁም እንዳዘዙት ሆነ።

፰ እና አማልክቱ ጠፈሩን ^ሰማይ ብለው ጠሩት። እንዲህም ሆነ ከምሽት እስከ ጠዋት ድረስ ሌሊት ብለው ጠሩት፤ ከጠዋት እስከ ምሽት ድረስም ቀን ብለው ጠሩት፤ እና ይህም ^ለሁለተኛ ጊዜ ሌሊትና ቀን ብለው ይጠሩት ነበር።

፱ እና አማልክት እንዲህ በማለት አዘዙ፥ ከሰማይ በታች ያሉት ^ውሀዎች ^በአንድ

፳፬ ፡ ^ሀ ቅ.መ.መ. ምድር—
ለሰው የተፈጠረች ነች።
ሓ ቅ.መ.መ. መፍጠር፣
ፍጥረት።
፳፭ ^ሀ ቅ.መ.መ. ታዛዥነት፣
ታዛዥ፣ መታዘዝ።
ለ ት.እና ቃ. ፲፯፡፲፪–፲፰፣
፲፯፡፲፡ ፲፭።
ቅ.መ.መ. ነጻ ምርጫ፤
የቤዛነት ዕቅድ።
፳፮ ^ሀ ይሁዳ ፩፡፮።
ለ ቅ.መ.መ. ስጋዊ፣ የሚሞት።
ሓ ቲቶ ፩፡፪።
ቅ.መ.መ. ክብር።
፳፯ ^ሀ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣
አምላክ—
እግዚአብሔር አብ።
ለ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ፤
የሰው ልጅ።
ሓ ሙሴ ፬፡፩–፪።
፳፰ ^ሀ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
ለ ቅ.መ.መ. የጥፋት ልጆች።
፳፱ ፩ ^ሀ ዘፍጥ. ፩፡፩፤
ሙሴ ፪፡፩።
ለ ቅ.መ.መ. መፍጠር፣
ፍጥረት።
፪ ^ሀ ዘፍጥ. ፩፡፪፤ ሙሴ ፪፡፪።
፣ ^ሀ ዘፍጥ. ፩፡፬–፣፤
ሙሴ ፪፡፬።
፡ ^ሀ ቅ.መ.መ. ሰማይ።
ለ ዘፍጥ. ፩፡፡።
፱ ^ሀ ዓም. ፱፡፣፤ ሙሴ ፪፡፣።
ለ ዘፍጥ. ፩፡፱።

ስፍራ ይከማቹ፣ እና ምድሩም ወጥቶ ይድ
ረቅ፤ እና እንዳዘዙትም እንዲህ ሆነ።
፲ እና አማልክቱ ደረቁን ምድር መሬት
ብለው አስታወቁ፤ እና በአንድነት የተሰበሰ
በውን ውሃ፣ ᐟᐟታላቅ ውሀዎች ብለው አስታ
ወቁት፤ እናም አማልክቱ ትእዛዛቸው እን
ደተከበሩ አዩ።
፲፩ አማልክቱም እንዲህ አሉ፡ ምድርን
ᐟᐟሳር እንድታሳድግ፤ ተክሎችም ዘር እን
ዲሰጡ፣ ፍሬ የሚያፈሩ ዛፎችም የራሳቸው
አይነት ፍሬዎች እንዲያፈሩ፣ ዘራቸውም
በምድር ላይ የእነርሱን አይነት እንዲሰጥ
እናዘጋጃቸው፤ እና እንዳዘዙትም እንዲህ
ሆነ።
፲፪ እና አማልክት ሳሮች ዘራቸው እን
ዲያመጡ፣ ተክል ከራሱ ዘር ተክልን እን
ዲያሳድግ፣ በራሱም አይነት ዘር እንዲ
ሰጥ፣ ምድርን አደራጁ፤ እና ምድርም ዛፍ
ከዘሯ እንድታሳድግ፣ ዘር እንድታፈራ፣
በዘርም የራሷን አይነት እንድታሳድግ፤
እና አማልክት ትእዛዛቸው እንደተከና
ወኑ አዩ።
፲፫ እና እንዲህ ሆነ ቀናትንም ቆጠሯ
ቸው፤ ከምሽት እስከ ጠዋት ድረስ ሌሊት
ብለው ጠሩት፤ እና እንዲህም ሆነ፣ ከጠዋት
እስከ ምሽት ድረስም ቀን ብለው ጠሩት፤
ይህም ሶስተኛው ጊዜ ነበር።
፲፬ እና አማልክት ᐟᐟብርሃናትን በሰማይ
ጠፈር አደራጁ፣ እና ቀን ከሌሊት እንዲ
ከፋፈሉ አደረጓቸው፤ እና ለምልክቶችና
ለዘመናት፣ እና ለቀናትና ለአመታት እን
ዲሆኑም አደራጁአቸው።
፲፭ እና በሰማይ ጠፈር ለምድር ብርሀን
እንዲሰጡ ብርሃናት እንዲሆኑ አደራጁአ
ቸው፤ እና እንዲህም ሆነ።
፲፮ አማልክትም ሁለት ᐟᐟታላቅ ብርሃናትን
አደራጁ፣ ታላቁን ብርሃን በቀን እንዲሰለ
ጥን፣ እና ታናሹን ብርሀን በሌሊት እንዲ
ሰለጥን፤ ከታናሹ ብርሀንም ጋር ከዋክብ
ትን አስቀመጡ፤
፲፯ አማልክትም ለምድር ብርሀንን እን
ዲሰጡ፣ እና ቀንንና ለሊትን እንዲያሰለ
ጥኑ፣ እናም ብርሀኑን ከጭለማ እንዲከፋ
ፍሉ፣ እነዚህን በሰማይ ጠፈሮች ላይ አስ
ቀመጧቸው።
፲፰ እና ያዘዙት እስከሚከናወኑም ድረስ
እነዚህን ነገሮች አማልክቱ ተመለከቱ።
፲፱ እና እንዲህ ሆነ ከምሽት እስከ ጠዋት
ድረስ ሌሊት ነበር፤ እንዲህም ሆነ ከጠዋት
እስከ ምሽት ድረስ ቀን ነበር፤ እናም ይህም
የአራተኛው ጊዜ ነበር።
፳ አማልክቱም አሉ፡ ውሀዎች ህይወት
ባላቸው ፍጡራን እንዲሞሉ ውሀዎችን
እናዘጋጅ፣ እና ወፎች ከምድር በላይ በሰ
ማይ ጠፈር እንዲበሩም እናዘጋጅ።
፳፩ እና አማልክት ታላቅ ᐟᐟአሳነባሪዎ
ችን፣ እና የሚርመሰመሱ ህይወት ያላ
ቸው ፍጡራንን፣ ውሀዎች እንደየወገና
ቸው በብዛት ውሀዎች እንዲያመጡ አዘ
ጋጁ፤ እና ክንፍ ያላቸውን ወፎች እንደየወ
ገናቸው። እና አማልክቱ ትእዛዛቸው እን
ደሚከናወኑ፣ እናም እቅዳቸው መልካም
እንደሆኑም አዩ።
፳፪ እና አማልክቱ አሉ፡ እንባርካቸዋ
ለን፣ እና እንዲበዙና እንዲባዙ እናደርጋ
ቸዋለን፣ እና የባህር ወይም ᐟᐟየታላቅ ውሃ
ዎችን ውሀ እንሞላቸዋለን፤ እና ወፎችንም
በምድር እንዲባዙ እናደርጋቸዋለን።
፳፫ እና እንዲህ ሆነ ከምሽት እስከ ጠዋት
ድረስ ሌሊት ብለው ጠሩት፤ እና እን
ዲህ ሆነ ከጠዋት እስከ ምሽት ድረስም ቀን
ብለው ጠሩት፤ እና ይህም የአምስተኛው
ጊዜ ነበር።
፳፬ እና ᐟᐟአማልክቱ ምድር ህያው ፍጡራ
ንን እንደወገናቸው፣ ከብቶችንና ተንቀሳ
ቃሾች ነገሮችን፣ እና የምድርን የዱር እን

፲ ᐟ ዘፍጥ. ፩፡፲፤ አብር. ፬፡፳፪።
፲፩ ᐟ ዘፍጥ. ፩፡፲፩–፲፪፤ ሙሴ ፪፡፲፩–፲፪።
፲፪ ᐟ ት. እና ቃ. ፹፰፡፲–፲፩።
፲፭ ᐟ ዘፍጥ. ፩፡፲፮።
፳፩ ᐟ ዘፍጥ. ፩፡፳፩፤ ሙሴ ፪፡፳፩።
፳፪ ᐟ አብር. ፬፡፲።
፳፬ ᐟ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ።

ስግት እንደወገናቸው እንዲመጡ አዘጋጁ አቸው፤ እንዳሉትም፣ እንዲህ ሆነ።

፲፱ አማልክት ምድር የዱር እንግት እን ደየወገናቸው፣ እና ከብቶችን እንደወገና ቸው፣ እና በምድር ላይ የሚሳቡ ፍጡራንን እንደየወገናቸው አደራጁ፤ እና አማልክት እንደሚታዘዙም አዩ።

፲፳ እና አማልክት [ሀ]ተመካከሩና እን ዲህ አሉ፥ እንሂድና [ለ]ሰውን በመልካችን፣ [ሐ]በአምሳላችን፣ እንስራ፤ እና በባህር ዓሶች፣ በሰማይ ወፎች፣ በከብቶች፣ እናም በምድር ሁሉ ላይ፣ እናም በምድር በሚንቀሳቀሱት ፍጡራን ሁሉ ላይ ስልጣን እንስጣቸው።

፲፳፩ ስለዚህ [መ]አማልክት ሰውን በእራሳ ቸው መልክ፣ በአማልክቱ መልክም እነ ርሱን፣ ወንድና ሴትን አድርገው አደራ ጁ ቸው።

፲፳፪ እና አማልክትም እንዲህ አሉ፥ እንባ ርካቸዋለን። እና አማልክትም እንዲህ አሉ፥ እንዲበዙና እንዲባዙ፣ እና ምድርንም እን ዲሞሏት፣ እና እንዲገዟት፣ እና የባህር ዓሶ ችን፣ እና የሰማይን ወፎች፣ እና በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትን ህያዋን ፍጡራንን ሁሉ እንዲገዟቸው እናደርጋለን።

፲፳፫ እና አማልክትም እንዲህ አሉ፥ እነሆ፣ በምድር ላይ የሚመጡትን ዘር የሚ ሰጡ ተክሎችን ሁሉ፣ እና ፍሬያቸው ያለ ባቸውን እያንዳንዱን ዛፎች ሁሉ እንሰጣቸ ዋለን፤ አዎን፣ ዘሮች የሚሰጡ የዛፍ ፍሬ ዎች እንሰጣቸዋለን፤ ይህም ለእነርሱ [መ]ምግ ባቸው ይሆናሉ።

፲፳ እና ለምድር አራዊት ሁሉ፣ እና ለሰ ማይ ወፎች ሁሉ፣ እና በምድር ላይ ለሚ ንቀሳቀሱ ህያዋን ፍጡራን ሁሉ፣ እነሆ፣ ህይወትን እንሰጣቸዋለን፣ እና እያንዳንዱን ለምለም ተክል ምግብ እንዲሆናቸው እን ሰጣቸዋለን፣ እና እነዚህ ነገሮች ሁሉ እን ደዚህ ይደራጃሉ።

፲፳፪ እና አማልክትም እንዲህ አሉ፥ ያል ናቸውን ነገሮች ሁሉ እናደርጋለን፣ እና እናደራጃቸዋለን፤ እና እነሆ፣ በጣም ታዛ ዦች ይሆናሉ። እና እንዲህ ሆነ ከምሽት እስከ ጠዋት ድረስ ብለው ጠሩት፤ እና እን ዲህ ሆነ ከጠዋት እስከ ምሽት ድረስም ቀን ብለው ጠሩት፤ እና [መ]ለስድስተኛ ጊዜ ቆጠ ሩት።

ምዕራፍ ፤

አማልክቱ ሁሉንም ነገሮች ለመፍጠር እቅዳቸውን ጨረሱ—እንደ እቅዳቸውም ፍጥረታቸውን አከናወኑ—አዳም ሁሉንም ህያዋን ፍጡራንን ስም ሰጠ።

፤ እና እንደዚህ ሰማያትንና ምድርን እናም በውስጣቸው ያሉትን ሁሉ እንደ ዚህ እንጨርሳለን።

፪ አማልክትም እርስ በራሳቸው እንዲህ ተባባሉ፥ [ሀ]በሰባተኛው ጊዜ የተማከርንባ ቸውን ስራችንን እንጨርሳለን፣ እና ከተ ማከርናቸው ስራዎችም በሰባተኛው ጊዜ እናርፋለን።

፫ እና አማልክት በሰባተኛው ጊዜ ከስራ ዎቻቸው በሙሉ እነርሱ (አማልክት) ለመ ስራት ከተመካከሩት [መ]ስለሚያርፉ በሰባተ ኛው ጊዜም ፈጸሙ፣ እና ይህን [ለ]ቀደሱት። እንደዚህም ነበር ሰማያትንና ምድርን ለመ ፍጠር በመካከላቸው የተመካከሩበትን በዚያ ጊዜ የወሰኑበት።

፬ እና አማልክት ወርደው ምድርንና ሰማ ያትን በፈጠሩበት ጊዜ፣ እነዚህን የሰማያ ትና የምድር ትውልዶችን ፈጠሩ፣

፭ ከምድር ውስጥ ከመሆኑ በፊት ስለእ ያንዳንዱ የሜዳ አትክልት፣ እና ስለእያ ንዳንዱ የለምለም ተክል ከማደጉ [ሀ]በፊት በሚመለከት ባሉት ሁሉ መሰረት፤ እነዚ ህን ለማድረግ ሲማከሩበትም አማልክት

፲፯ [ሀ] ቅ.መ.መ. ምክር (ስም)።
[ለ] ሙሴ ፮፡፳–፲።
[ሐ] ቅ.መ.መ. ሰው፣ ሰዎች።
፲፯ [ሀ] ዘፍጥ. ፩፡፲፯–፲፰፤
አብር. ፩፡፲።
፲፱ [ሀ] ዘፍጥ. ፩፡፲፱–፳።
፳፩ [ሀ] ዘፀአ. ፳፩፡፲፯።
፲ [ፀ] [ሀ] ቅ.መ.መ. የሰንበት ቀን።
[ሀ] ዘፀአ. ፳፡፳–፲፩፤
ሞዛያ ፲፫፡፲፯–፲፱።
[ለ] ት. እና ቃ. ፫፲፯፡፲፪።
[ሀ] ቅ.መ.መ. የመንፈስ ፍጥረት።

ከመፅሐፈ አብርሐም ቅርፅ

ቁጥር ፲

መግለጫ

ስዕል ፩ በንጉሱ ትሁትነት፣ አብርሐም የሰማይ ታላቅ አመራር አርማ የሆነውን ክህነት የሚወክለውን ዘውድ በራሱ ላይ ተደርጎለት፣ የፍርድና የፍትሕ በትረ መንግስት በእጁ ይዞ፣ በፈርዖን ዙፋን ላይ ተቀምጦ።

ስዕል ፪ ስሙ በፊደል ከራሱ በላይ የተጻፈለት ንጉስ ፈርዖን።

ስዕል ፫ በስዕል ፤ ላይ እንደተሰጠው አብርሐም በግብፅ ውስጥ የሚያስመለክት።

ስዕል ፬ ከእጅ በላይ እንደተጻፈው፣ የግብፅ ንጉስ ፈርዖን ልውል።

ስዕል ፭ ከእጁ በላይ በፊደል በተጻፈው እንደሚወከለው፣ የንጉሱ ዋና አስተናጋጅ ሹለም።

ስዕል ፮ የልውሱ ንብረት ባሪያ አሊምላኽ።

አብርሐም በንጉሱ አደባባይ ውስጥ ስለ ስነ ፈለክ ጥናት መሰረታዊ መርሆች ሲሟገት።

በምድር ላይ እንዲዘንብ አላደረጉም፣ እና
ሰውም መሬትን እንዲያርስ አልሰሩትምና።
፲፤ ነገር ግን ከምድር ጭጋግ ወደላይ ወጣ፣
እና ውሀ የምድርን ገጽ አረሰረሰ።
፲፩ እና አማልክት ሰውን [ሀ]ከአፈር [ለ]አበ
ጁት፣ እና [ሐ]መንፈሱን (ይህም ማለት የሰ
ውን መንፈስ) ወሰዱና እርሱ ውስጥ ጨመ
ሩት፤ በአፍንጫውም የህይወትን እስትን
ፋስ እፍ አሉበት፣ እና ሰውም ህያው ሕፃስ
ሆነ።
፲፪ አማልክትም በምስራቅ [መ]በዔድን ገነ
ትን አዘጋጁ፣ እና በሰሩት ሰውነት ውስጥ
መንፈሱን የጨመሩበትን ሰው በዚያም አስ
ቀመጡት።
፲፫ እና ለአይን የሚያስደስት ለመብልም
መልካም የሆኑ እያንዳንዱን ዛፍ አማልክቱ
ከመሬት ውስጥ ፈጠሩ፣ ደግመውም በገ
ነት መካከልም [ሠ]የህይወት ዛፍ፣ እና የመ
ልካምና ክፉ እውቀት ዛፍ።
፲፬ የአትክልት ስፍራውን የሚያጠጣ ወንዝ
ከዔድን ይፈስ ነበር፣ ከዚያም በአራት ተከ
ፍሎአል እና አራት ራሶች ሆኗል።
፲፭ አማልክትም ሰውን ወሰዱ እና እንዲ
ያለመልማትና እንዲጠብቃት በዔድን ገነት
ውስጥ አስቀመጡት።
፲፮ አማልክትም ሰውን እንዲህ ብለው
አዘዙት፥ በአትክልት ስፍራ ውስጥ ከሚ
ገኘው ከማንኛውም ዛፍ ፍሬ ለመብላት ነጻ
ነህ፣
፲፯ ነገር ግን ከመልካምና ክፉ እውቀት
ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን በእር
ግጥም ትሞታለህ። አሁን እኔ አብርሐም
ጊዜው [ሀ]በቆሎብ መቆጠሪያ ጊዜ በሆነው
በጌታ [ለ]ጊዜ እንደሆነ አየሁ፤ እስከዚህም
ጊዜ ድረስ አማልክቱ ለአዳም ጊዜ ማወ
ቂያ አልሰጡትም ነበርና።
፲፰ እና አማልክቱም እንዲህ አሉ፥ ለሰው
የሚመች ረዳት እንፍጠርለት፣ ሰው ብቻ
ውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለምና፣
ስለዚህ የሚመች ረዳት እንፍጠርለት።
፲፱ እና አማልክቱ [መ]በአዳም ከባድ እን
ቅልፍን ጣሉበት፤ አንቀላፋም፣ እና ከጎ
ኑም አንዲት አጥንትን ወሰዱና ስፍራውን
በሥጋ ዘጉ፤
፲፲ አማልክቱም ከአዳም የወሰዱትን አጥ
ንት [ሠ]ሴት አድርገው ሠሯት፣ ወደ አዳምም
አመጧት።
፲፲ አዳምም እንዲህ አለ፥ ይህች አጥንት
ከአጥንቴ፣ ስጋዋም ከስጋዬ ናት፤ ከወንድ
ተገኝታለችና ሴት ትባላለች፤
፲፲ ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተ
ዋል፣ እና ከሚስቱም [ይ]ጣበቃል፣ ሁለ
ቱም [ለ]አንድ ሥጋ ይሆናሉ።
፲፲ ሰውና ሚስቱም፣ ሁለቱም ራቁታቸ
ውን ነበሩ፣ አይተፋፈሩም ነበር።
፳ አማልክቱም የምድር አራዊትንና
የሰማይ ወፎችን ሁሉ ከመሬት አደረጉ፤
በምን ስም እንደሚጠራቸውም ያዩ ዘንድ
ወደ አዳም አመጧቸው፤ አዳምም ሕያው
ነፍስ ላለው ሁሉ በስሙ እንደ ጠራው ስሙ
ያው ሆነ።
፳፩ አዳም ለከብቶች፣ ለሰማይ ወፎች፣
ለዱር አራዊት ሁሉ ስም አወጣ፤ እናም
ለአዳም የሚመች ረዳት ተገኘለት።

፲፤ ሀ ሙሴ ፩፡፳፭፤ ፤ ፶፡፶፩።
ለ አብር. ፩፡፳፤–፴፩።
ሐ ዘፍጥ. ፪፡፲፤
ት. እና ቃ. ፶፫፡፴፫።
ቅ.መ.መ. መንፈስ፤
ቅድመ ምድራዊ ህይወት።
መ ቅ.መ.መ. ነፍስ።
፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. ዔድን።
፩ ሀ ቅ.መ.መ. የህይወት ዛፍ።
፲፫ ሀ አብር. ፫፡፪–፩።
ቅ.መ.መ. ቆሎብ።
ለ ፪ ጴጥ. ፫፡፰።
፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. አዳም።
፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. ሔዋን።
፲፰ ሀ ት. እና ቃ. ፶፪፡፳፪፤
፶፬፡፲፭–፲፯።
ለ ቅ.መ.መ. ጋብቻ፣ መጋባት።

ጆሴፍ ስሚዝ—ማቴዎስ

በ፲፰፻፴፭ (እ.አ.አ.) ለነብዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተገለጠለት የመፅሐፍ ቅዱስ ትርጉም ልዩ እትም፥ ማቴዎስ ፳፫፣ ፳፬ እና ምዕራፍ ፳፭።

ኢየሱስ በኢየሩሳሌም ላይ ስለሚመጣው ጥፋት አስቀድሞ ነገራቸው—ስለሰው ልጅ ስለክፉው መጥፊያ ዳግም ምፅዓት፣ እና ስለክፉዎች ጥፋት አስተማረ።

እላችኋለሁና፣ በጌታ ስም በሰማይ ደመናዎች ውስጥ፣ እና ሁሉም ቅዱስ መላእክት ከእርሱም ጋር [a]የሚመጣ የተባረከ ነው እስክትሉ ድረስ ከእንግዲህ ወዲህ አታዩኝም እና በነቢያት ስለእርሱ ነው የተጻፈው ብላችሁ ልታውቁኝ አትችሉም። ከዚያም ደቀ መዛሙርቱ [b]በእግዚአብሔር ቀኝ እጅ በኩል በክብር ዘውድ ተጭኖለት ዳግም ተመልሶ እንደሚመጣ ገባቸው።

፪ ኢየሱስ ከቤተ መቅደስ ወጥቶ ሄደ፤ እና ደቀ መዛሙርቱም የሚለውን ለመስማት ወደእርሱ መጥተው እንዲህ አሉ፥ መምህር፣ ስለቤተመቅደሱ ህንጻ አሳየን፣ አንተ እንዳልከው—እነርሱም ይፈርሳሉ፣ እና የተፈታ ሆኖ ትቀርላቸዋለች።

፫ ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፥ እነዚህን ነገሮች ሁሉ አታዩም፣ እና አይገቧችሁ ምን? እውነት እላችኋለሁ፣ ከዚህ ቤተመቅደስ [c]ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ በዚህ የሚቀር አይኖርም።

፬ እና ኢየሱስ ትቶአቸው ሄደ፣ እና ወደ [d]ደብረ ዘይት ተራራም ሄደ። በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ተቀምጦ ሳለ፣ ደቀ መዛሙርቱ ለብቻቸው ወደ እርሱ ቀርበው፣ ስለ ቤተመቅደሱ መፍረስና ስለ አይሁድ በተመለከተ ያልካቸው እነዚህ ነገሮች መቼ እንደ ሚሆኑ ንገረን፤ እና የአንተ [e]ደግሞ መመለሻና [f]የአለም መጨረሻ፣ ወይም የአለም መጨረሻ የሆነው [g]የክፉዎቹ መጥፊያ [h]ምልክትስ ምንድን ነው? አሉት።

፭ እና ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፥ ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ፤

፮ ብዙዎች በስሜ—እኔ ክርስቶስ ነኝ—በማለት ይመጣሉና፣ እና ብዙዎችንም ያስታሉ፤

፯ ከዚያም በስሜ ምክንያትም [i]ለመከራ አሳልፈው ይሰጧችኋል፣ እናም ይገድሏ ችኋል፣ እናም በህዝብ ሁሉ ዘንድ [j]የተጠላችሁ ትሆናላችሁ፤

፰ እና ብዙዎችም ይቀየማሉ፣ እና እርስ በራስ ይክዳሉ፣ እርስ በራስም ይጣላሉ፤

፱ እና ብዙ ሐሰተኛ ነቢያትም ይነሳሉ፣ እና ብዙዎችንም ያስታሉ፤

፲ እና ክፋት በብዛት ስለሚገኝ፣ የብዙዎ ችም [k]ፍቅር ትቀዘቅዛለች፤

፲፩ በፅናት የሚቋቋመውና የማይሸነፈው ግን፣ እርሱ ይድናል።

፲፪ [l]ኢየሩሳሌምን በሚመለከት በጥፋት ነቢዩ [m]ዳንኤል የተናገረውን የጥፋት [n]ርኩሰት ስታዩ፣ ከዚያም [o]በተቀደሰ ስፍራም ቁሙ፤ ይህን የሚያነብ ይግባው።

፲፫ ከዚያም በይሁዳ የሚገኙ ወደ [p]ተራሮች ይሽሹ፤

፩ ፩ *ሀ* ማቴ. ፳፭፥፳፯፤
የሐዋ. ፩፥፲፩።
ለ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣
አምላክ።
፫ *ሀ* ሉቃ. ፲፱፥፵፬።
፬ *ሀ* ቅ.መ.መ. ደብረ ዘይት ተራራ።
ለ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ
ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
ሐ ቅ.መ.መ. አለም—
የአለም መጨረሻ።
መ ሚል. ፬፥፭፤
ት. እና ቃ. ፲፴፫፥፳፬–፳፭።
ቅ.መ.መ. ክፉ፣ ክፋት።
ሠ ሉቃ. ፳፩፥፯–፴፤
ት. እና ቃ. ፵፭፥፲፯–፳፭።
ቅ.መ.መ. የመጨረሻ ቀናት፣
የኋለኛው ቀናት፤
የጊዜዎች ምልክቶች።
፯ *ሀ* ፩ ጴጥ. ፬፥፲፪–፲፬።
ለ ቅ.መ.መ. ማሳደድ፣
መሳደድ።
፲ *ሀ* ት. እና ቃ. ፵፭፥፳፯።
፲፪ *ሀ* ቅ.መ.መ. ኢየሩሳሌም።
ለ ቅ.መ.መ. ዳንኤል።
ሐ ዳን. ፲፪፥፲፩።
መ ት. እና ቃ. ፲፩፥፳፪–፳፭።
፲፫ *ሀ* ት. እና ቃ. ፲፴፫፥፲፫።

፲፬ በቤቱ ጣራ ላይ የሚገኝ ማንም ሰው
እቃውን ከቤቱ ለማውጣት አይውረድ፤
፲፭ በእርሻም ያለ ልብሱን ይወስድ ዘንድ
ወደ ኋላው አይመለስ።
፲፮ በዚያችም ወራት ᵐለርጉዞችና ለሚያ
ጠቡ ወዮላቸው፤
፲፯ ነገር ግን ሽሽታችሁ በክረምት ወይም
በሰንበት እንዳይሆን ጸልዩ፤
፲፰ በዚያን ጊዜ ከመንግስታቸው መጀመ
ሪያ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ከእግዚአብሔር
ወደ እስራኤል ተልኮ ያልነበረ ታላቅ ስቃይ
ᵐበአይሁዶች፣ እና ᵃበኢየሩሳሌም ኗሪዎች
ላይ ይደርሳል፤ ከዚህም በኋላ በእስራኤል
ላይ እንደገና አይላክም።
፲፱ እነርሱ ላይ የደረሱባቸው ገና ከሚመ
ጡባቸው ሀዘን የመጀመሪያዎቹ ናቸው።
፳ እና እነዚያ ቀናትስ ካላጠሩ በስተቀር፣
ᵐᵓᵓ ከለበሰ የሚድን ማንም አይኖርም፤
ነገር ግን እነዚያ ቀናት ለተመረጡ ሰዎች፣
በቃል ኪዳን መሰረት፣ ያጥራሉ።
፳፩ አይሁዶችን በሚመለከት የነገረኳ
ችሁ እነዚህን ነገሮች ተመልከቱ፤ ደግ
ሞም በኢየሩሳሌም ላይ ከሚመጡት ከእ
ነዚያ ቀናት በኋላ፣ ማናችሁም አስተውሉ
ክርስቶስ በዚህ አለ ወይም በዚያ አለ ቢላ
ችሁ አትመኑ፤
፳፪ በእነዚያ ቀናት ሐሰተኞች ክርስቶሶ
ችና ሐሰተኞች ነቢያትም ይነሣሉና፣ ቢቻ
ላቸውም፣ በቃል ኪዳን መሰረት ምርጥ የነ
በሩትን፣ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ
ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅን ያሳያሉ።
፳፫ እነሆ፣ እነዚህን ነገሮች የምነግራችሁ
ᵐለተመረጡት ጥቅም ነው፤ ᵃጦርንም የጦ
ርንም ወሬ ትሰማላችሁ፤ አትጨነቁም፣
የነገርኳችሁ ሁሉ መፈጸም አለባቸውና፤
ነገር ግን መጨረሻው ገና ነው።
፳፬ እነሆ፣ አስቀድሜ ነግሬአችኋለሁ፤
፳፭ ስለዚህ፣ እነሆ፣ በበረሀ ነው ቢሉአ
ችሁ፣ አትውጡ፥ እነሆ፣ በእልፍኝ ነው
ቢሉአችሁ፣ አትመኑ፤
፳፮ የጠዋት ብርሀን ᵐከምሥራቅ ወጥቶ
እስከ ምዕራብ እንደሚያበራ፣ እና ምድርን
በሙሉ እንደሚሸፍን፣ የሰው ልጅ ምፅዓ
ትም እንዲሁ ይሆናልና።
፳፯ አሁንም ምሳሌ አሳያችኋለሁ። እነሆ፤
ቅሪቶች ባሉበት፣ አሞራም አብረው ᵐይሰ
በሰባሉ፣ እንደዚህም የእኔ ምርጦች ከአራቱ
የምድር ማዕዘናት ይሰበሰባሉ።
፳፰ እና ጦርንም የጦርንም ወሬ ይሰማሉ።
፳፱ እነሆ፣ የምናገረው ለምርጦቼ ጥቅም
ነው፤ ሕዝብ በሕዝብ ላይ መንግሥትም
በመንግሥት ላይ ይነሣልና፣ ᵐራብም ቸነ
ፈርም የምድርም መናወጥ በልዩ ልዩ ስፍራ
ይሆናል፤
፴ ደግሞም ከዓመፃ ብዛት የተነሣ የሰዎች
ፍቅር ትቀዘቅዛለች፤ እስከ ፍጻሜው የሚ
ጸና ግን እርሱ ይድናል።
፴፩ ደግሞም፣ ለአሕዛብም ሁሉ ምስክር
እንዲሆን ይህ የመንግሥት ወንጌል ᵐበዓለም
ሁሉ ይሰበካል፣ በዚያን ጊዜም መጨረሻው
ወይም የክፋተኞቹ ጥፋት ይመጣል።
፴፪ ደግሞም በነቢዩ በዳንኤል የተነገረው
የጥፋት ርኩሰትም ይፈጸማል።
፴፫ ከዚያች መከራ ቀናት በኋላ ወዲያው
ᵐፀሐይ ትጨልማለች፣ ጨረቃም ብርሃን
ዋን አትሰጥም፣ ከዋክብትም ከሰማይ ይወ
ድቃሉ፣ እና የሰማይ ሀይላትም ይናወጣሉ።
፴፬ በእውነት እላችኋለሁ፣ የነገርኳችሁ
ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ፣ እነዚህ ነገሮች
የሚታዩባቸው ይህ ትውልድ አያልፍም።
፴፭ ምንም እንኳን ሰማይና ምድር የሚ
ያልፉበት ቀን ቢመጣም፣ ᵐቃሌ ግን አያል
ፍም፣ ነገር ግን ሁሉም ይፈጸማሉ።
፴፮ አስቀድሜ እንዳልኳችሁ፣ ከዚያች
ᵐየመከራ ቀናት በኋላ የሰማያትም ኃይላት
ይናወጣሉ፣ በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ

፲፮ ᵐ ሉቃ. ፳፫፡፳፱–፴።
፲፰ ᵐ ቅ.መ.መ. አይሁዶች።
ᵃ ዘካ. ፲፪፣ ፲፬፡፩–፭።
፳፫ ᵐ ቅ.መ.መ. ምርጦች።
ᵃ ት. እና ቃ. ፴፭፡፳፯።
፳፭ ᵐ ሕዝ. ፴፫፡፪።
፳፯ ᵐ ቅ.መ.መ. እስራኤል—
የእስራኤል መሰብሰብ።
፳፱ ᵐ ት. እና ቃ. ፴፫፡፳ፀ–፳፭።
፴፩ ᵐ ማቴ. ፳፡፲፱–፳።
፴፫ ᵐ ኢዩ. ፪፡፲፣
ት. እና ቃ. ፳፱፡፲፬።
፴፭ ᵐ ት. እና ቃ. ፩፡፴፰።
፴፮ ᵐ ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፡፲፰።

ምልክት በሰማይ ይታያል፣ ከዚያም የም
ድር ወገኖች ሁሉ ዋይ ዋይ ይላሉ፤ የሰው
ልጅንም በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ
ደመና ^ሲመጣ ያዩታል፤
ሚ፣ እና ᵛቃላቶቼን እንደ ሀብት የሚ
ያከማቸው ማንም አይታለልም፣ የሰው
ልጅም ይመጣልና፣ እና ^መላእክቱንም
ከታላቅ መለከት ድምፅ ጋር ይልካቸ
ዋል፣ ከሰማያትም ዳርቻ እስከ ዳርቻው
ከአራቱ ነፋሳት ለእርሱ የተመረጡትን
ᵃይሰበስባሉ።
ሚ፪ አሁን ᵛየበለስ ዛፍን ምሳሌ ተማሩ—
ቅርንጫፍዋ ሲለሰልስ ቅጠልዋም ሲያ
ቈጠቍጥ፣ ያን ጊዜ በጋ እንደ ቀረበ ታው
ቃላችሁ፤
ሚ፫ እንደዚሁም እነዚህን ሁሉ ምርጦቼ
ሲያዩ፣ እርሱ በደጅ እንደቀረበ፣ እንዲ
ሁም በበር ላይ እንዳለ ያውቃሉ፤
ሚ፬ ስለዚያች ቀንና ሰዓት ግን ከአባቴ በቀር
የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ማንም ᵛየሚያ
ውቅ የለም።
ሚ፭ ᵛበኖህ ዘመን እንደ ነበረ፣ የሰው ልጅ
መምጣትም እንዲሁ ይሆናል፤
ሚ፮ ᵛከጥፋት ውሃ በፊት እንደነበረም
ይሆንላቸዋል፤ ኖህ ወደ መርከቡ እስከገባ
በት ቀናት ድረስም ሲበሉና ሲጠጡ፣ ሲያ
ገቡና ሲጋቡ ነበሩና፤
ሚ፯ እና የጥፋት ውኃም መጥቶ፣ ሁሉን
እስከ ወሰዳቸው ድረስ አላወቁም፤ የሰው
ልጅ መምጣትም ደግሞ እንዲሁ ይሆናል።
ሚ፰ ከዚያም የተጻፈው ይፈጸማል፣ ᵛበመ
ጨረሻዎቹም ቀናት ሁለት ሰዎች በዕርሻ
ላይ ይሆናሉ፣ አንዱ ይወሰዳል ሌላው
^ይቀራል፤
ሚ፱ ሁለቱ በወፍጮ ይፈጫሉ፣ አንዱ
ትወሰዳለች ሌላዋ ትቀራለች።
ሚ፲ እና እኔ ለአንዱ የምለውን፣ ለሁሉም
ሰዎች እላለሁ፤ ጌታችሁ በምን ሰዓት እን
ዲመጣ አታውቁምና እንግዲህ ᵛንቁ።
ሚ፲፩ ያን ግን እወቁ፤ ባለቤት ከሌሊቱ በየ
ትኛው ክፍል ሌባ እንዲመጣ ቢያውቅ ኖሮ፣
ይነቃ ነበር፣ እና ቤቱም እንዲፈርስ አይፈ
ቅድም ነበር፣ ነገር ግን ይዘጋጅም ነበር።
ሚ፲፪ ስለዚህ እናንተ ደግሞ ተዘጋጁ፣
የሰው ልጅ በማታስቡበት ሰዓት ይመጣ
ልና።
ሚ፲፫ በተገቢው ጊዜ ምግባቸውን እንዲ
ሰጣቸው ባለቤቱ በቤተሰቦቹ ላይ የሾመው
ᵛታማኝና ብልህ አገልጋይ ያደረገው እን
ግዲህ ማን ነው?
ሚ፲፬ ባለቤቱ ተመልሶ ሲመጣ እንዲህ ሲያ
ደርግ የሚያገኘው ያ ባሪያ የተባረከ ነው፤
እና እውነት እላችኋለሁ፣ በእቃዎቹ ሁሉ
ላይ ገዢ እንዲሆን ይሾመዋል።
ሚ፲፭ ነገር ግን ያ ክፉ ባርያ በልቡ እንዲህ
ቢል፥ ጌታዬ መመለሻው ᵛይዘገያል፣
ሚ፲፮ እና የባልንጀሮቹን ባሮች ሊመታ፣ እና
ከሰካሮችም ጋር ሊበላና ሊጠጣ ጀመረ፣
ሚ፲፯ የዚያ ባርያ ጌታ ባልጠበቃት ቀን፣ እና
ባላወቃትም ሰዓት ይመጣል፣
ሚ፲፰ ከሁለትም ይሰነጥቀዋል፣ እና እድሉ
ንም ከግብዞች ጋር ያደርግበታል፤ በዚያ
ልቅሶና ጥርስ ᵛማፋጨት ይሆናል።
ሚ፲፱ በሙሴ ትንቢት መሰረት፣ እንደዚህም
የክፉዎች መጨረሻ ይመጣል፣ ብሏል፥
ከሰዎች መካከል ይቆረጣሉ፤ ነገር ግን የም
ድር ᵛመጨረሻው ገና አይደለም፣ ነገር ግን
ከጥቂት ጊዜ በኋላ ነው።

ሚ፲፩ ^ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
ሚ፲፪ ᵛ ቅ.መ.መ. ቅዱሳት መጻህፍት።
^ ት. እና ቃ. ፳፱፡ ፲፩–፲፭።
ᵃ ቅ.መ.መ. እስራኤል—የእስራኤል መሰብሰብ።
ሚ፲፫ ᵛ ት. እና ቃ. ሚ፲፭፡ ፲፲፮።
ᵛ ᵛ ት. እና ቃ. ሚ፲፱፡ ፳–፳፩፣ ሚ፲፱፡ ፯።
ሚ፲፩ ᵛ ዘፍጥ. ፮፡ ፭።
ሚ፲፪ ᵛ ቅ.መ.መ. የኖኅ ዘመን የጥፋት ውሀ።
ᵛ ᵛ ቅ.መ.መ. የመጨረሻ ቀናት፣ የኋለኛው ቀናት።
^ ዘካ. ፲፫፡ ፰።
ᵛ ᵛ ቅ.መ.መ. መጠበቅ፣ ጠባቂ።
ᵛ ᵛ ቅ.መ.መ. መታመን።
ᵛ ᵛ ት. እና ቃ. ሚ፲፭፡ ፳፲፮።
ᵛ ᵛ ማቴ. ፳፡ ፲፪።
ᵛ ᵛ ᵛ ᵛ ኔፊ ፴፡ ፲፣ ት. እና ቃ. ፩፡ ፱–፲፣ ፳፱፡ ፲፲፮።
ᵛ ᵛ ቅ.መ.መ. አለም—የአለም መጨረሻ።

የጆሴፍ ስሚዝ—ታሪክ

ከነብዩ ጆሴፍ ስሚዝ ታሪክ የተወሰደ

ጆሴፍ ስለትውልዱ፣ ስለቤተሰብ አባ ላቱ፣ እና ከጊዜው ቅድሚያ መኖሪያቸው ተናገረ—በምዕራብ ኒው ዮርክ ውስጥ ልዩ በሀይማኖት መነሳሳት ተሰራጨ—በያዕቆብ እንደተመራው ጥበብን ለመፈለግ ወሰነ—አብና ወልድ ታዩት፣ እና ጆሴፍ ወደነብ ያዊ አገልግሎቱ ተጠራ። (አንቀፅ ፩–፳፡)

የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ᵐቤተክርስቲያን ᵃአነሳስ እና እድገትን በሚመለከት በክፋት በተጠመዱ እና መሰሪ ሰዎች የተሰራጩትን የዚህችን ጻባይ ላይ በጸሀፊዎቹ ስሟን እንደ ቤተክርስቲያን እና በአለም እያደገች እያለች ለማጥፋት ያቀዱባቸውን ብዙ ሀተታዎችን ለማስተዋወቅ—ይህን ታሪክ ለመጻፍ፣ የህዝብን አዕምሮ ለማረጋጋት፣ እና እውነት ለሚፈልጉት ሁሉ፣ እነዚህ ተጨባጭ ነገሮች እንዳሉኝ፣ በእኔ እና በቤተክርስቲያኗ በሚመለከት ያለፉትን ተጨባጭ ነገሮችን ለመስጠት ተገፋፍቼ ነበር።

፪ በዚህ ታሪክ ውስጥ፣ በእውነት እና በፅድቅ፣ አስቀድመው እንደነበሩ፣ ወይም አሁንም እንዳሉት፣ ከአሁን [፲፰፻፴፰ (እ.አ.አ.)] ይህች ቤተክርስቲያን ᵐከተደራጀችበት ስምንት አመት ጀምሮ ቤተክርስቲያኗን በሚመለከት የነበሩትን የተለያዩ ሁኔታዎች አቀርባለሁ።

፫ ᵐየተወለድኩት በጌታችን አመት አንድ ሺህ ስምንት መቶ አምስት፣ በታህሳስ ሀያ ሶስት ቀን (እ.አ.አ.)፣ በሼረን ከተማ፣ በውንድሰር የግዛት ክፍል፣ በቨርሞንት ስቴት ውስጥ ነበር። . . . በአስር አመቴ ወይም በዚያ አካባቢ፣ አባቴ ᵃጆሴፍ ስሚዝ፣ ቀዳማዊ የቨርሞንት ስቴትን ተወ፣ እና ወደፓልማይራ፣ በኦንታሪዮ (አሁንም ዌይን በሚባለው) የግዛት ክፍል፣ ወደ ኒው ዮርክ ስቴት ውስጥ ሄደ። አባቴ ፓልማይራ ውስጥ ከደረሰ አራት አመታት በኋላ፣ ከቤተሰቡ ጋር ወደ ማንቸስተር በአንድ አይነት ኦንታሪዮ የግዛት ክፍል ሄደ።

፬ ቤተሰቡ አስራ አንድ ነፍሳት ያሉበት፣ ስማቸውም አባቴ ᵐጆሴፍ ስሚዝ፣ ᵃእናቴ ሉሲ ስሚዝ (ስሟ ከመጋባቷ በፊት ማክ፣ የሰለሞን ማክ ሴት ልጅ፣ ነበረች)፣ ወንድሜ ᵃአልቨን (በህዳር ፲፱ ቀን ፲፰፻፲፰ [እ.አ.አ.] በ፳፤ አመቱ የሞተው)፣ ᵐሀይረም፣ ራሴ፣ ᵐሳሙኤል ሀሪሰን፣ ውልያም፣ ዶን ካርሎስ፣ እና እህቶቼ ሰፍሮንያ፣ ካትሪን፣ እና ሉሲ. ነበሩ።

፭ ወደ ማንቸስተር ከሄድን በሁለተኛው አመት አካባቢ፣ በምንኖርበት ስፍራ ውስጥ ሀይማኖትን በተመለከተ ያልተለመደ የመነሳሳት ስሜት ነበረ። በመተዲስት ተጀመረ፣ ነገር ግን ወዲያውም በሀገሪቱ ባሉ ክልሎች ውስጥ በሁሉም ሀይማኖቶች መካከል የተሰራጨ ሆነ። በእርግጥ የሀገሩ ዲስትሪክት በሙሉ በዚህ የተነኩ ይመስል ነበር፣ እና ታላቅ ቁጥር ያላቸው ሰዎች በተለያዩ የሀይማኖት ቡድኖች ራሳቸውን አባል አድርገው ነበር፣ ይህም በሰዎች መካከል አንዳንዶች ᵐ“እንኳን በዚህ!” እና ሌሎች “እንኳን በዚያ!” በማለት በመጮህ፣ ትንሽ ያልሆነ ሁከትን እና መከፋፈልን ፈጥሮ ነበር።

፩ ፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን።
ለ ቅ.መ.መ. የወንጌል ዳግም መመለስ።
፪ *ሀ* ት. እና ቃ. ፳፣ ፩።
፫ *ሀ* ቅ.መ.መ. ስሚዝ፣ ጆሴፍ ዳግማዊ።
ለ ፪ ኔፊ ፫፣ ፲፭።
፬ *ሀ* ቅ.መ.መ. ስሚዝ፣ ጆሴፍ ቀዳማዊ።
ለ ቅ.መ.መ. ስሚዝ፣ ሉሲ ማክ።
ሐ ት. እና ቃ. ፲፴፯፣ ፴–፴፡
መ ቅ.መ.መ. ስሚዝ፣ ሀይረም።
ሠ ቅ.መ.መ. ስሚዝ፣ ሳሙኤል ኤች።
፭ *ሀ* ማቴ. ፳፤፡፣ ፳፫፡

አንዳንዶች የሜተድስት፣ አንዳንዶች የፕረስብተሪያን፣ እና ሌሎች የባፕቲስት ሀይማኖትን የሚደግፉ ነበሩ።

፲፯ በሚቀየሩበት ጊዜ እነዚህ የተለያዩ ሀይማኖቶች ተቀያሪዎች ታላቅ ፍቅርን የሚገልጹ ቢሆኑም፣ እና በመነሳት እና ይህን አስደናቂ የሀይማኖት ስሜት ትእ ይንትን የሚያበረታቱ እነዚያ ቀሳውስ ትም፣ ሁሉንም በፈለጉት የሀይማኖት ወገን አባል እንዲሆኑ ለመቀየር ታላቅ ጉጉትን ቢያሳዩም፤ ነገር ግን የተቀየሩት አንዳን ዶቹ ወደ አንድ ቡድን እና አንዳንዶችም ወደ ሌሎች፣ ተለይተው ሲሄዱ፣ የቀሳው ስቱም ይሁን የተቀየሩት ሰዎች መልካም ስሜት ከእውነተኛነት ይልቅ የማስመሰል በመሆኑ ታላቅ ግራ መጋባት እና መጥፎ ስሜት አይሷል—ቁስ ከቁስ፣ እና የተለ ወጡትም ከጠለወጡት ጋር ክርክር ውስጥ ነበሩ፤ ስለዚህ አንድ ለሌላ የነበራቸው ጥሩ ስሜት ሁሉ፣ ይህም ቢኖር፣ በቃላት *ሠ*ጠብ እና በአስተሳሰብ ፉክክር በሙሉ ጠፍተው ነበር።

፲፰ በዚህ ጊዜ በአስራ አምስት አመቴ ላይ ነበርኩኝ። የአባቴ ቤተሰብ በፕረስብተሪያን ሀይማኖት ለአባልነት ተመልምለው ነበር፣ እና አራቱ የዚያ ቤተክርስቲያን አባል ሆኑ፣ እነርሱም እናቴ ሉሲ፣ ወንድሞቼ ሀይረ ምና ሳሙኤል ሀርሰን፣ እና እህቴ ሰፍሮ ንያ ነበሩ።

፲፱ በዚህ ታላቅ መነሳሳት ጊዜ አዕምሮዬ በጥብቅ ሀሳብና ታላቅ ችግር ላይ ተነሳስቶ ነበር፤ ነገር ግን ምንም እንኳን ስሜቴ ጥልቅ እና በአብዛኛውም ጊዜ ሀያል ቢሆንም፣ የሆነ ሆኖም ከእነዚህ ቡድኖች ሁሉ ራሴን ገለልተኛ አደረግሁኝ፣ ይህም ቢሆን በተ ቻለ መጠን ዘወትር በተለያዩ ስብሰባዎቻ ቸው እገኝ ነበር። ከጊዜም በኋላ አዕምሮዬ የሜተድስት ሀይማኖት ደጋፊ እየሆነ መጣ፣ እና ከእነርሱም ጋር አንድ ለመሆን ፍላ ጎት ተሰማኝ፤ ነገር ግን በተለያዩ ሀይማኖ ቶች መካከል ክርክሩ እና ጠቡ ታላቅ ስለ ነበረ፣ እንደ እኔ ወጣት እና በሰዎች እና ነገ ሮች ልምድ የሌለው ሰው የትኛው ትክክ ለኛ እና የትኛው ስህተተኛ እንደሆነ በም ንም በእርግጠኝነት የምወስንበት መንገድ አልነበረም።

፳ ጩኸት እና ሁከታው ታላቅ እና የማያ ቆም ስለነበረ፣ በየጊዜው አዕምሮዬ በጣም የተነሳሳ ነበር። የፕረስብተሪያኖች ባፕቲ ስት እና ሜተዲስቶቹን በጣም የተቃወሙ ነበሩ፣ እና የመረዳት ችሎታና ጥበብ ሀይ ሎችን በሙሉ ስህተቶቻቸውን ለማረጋ ገጥ ወይም ሰዎች እነርሱ የተሳሳቱ እን ደሆኑ እንዲያስቡ ለማድረግ ይጥሩ ነበር። በሌላም በኩል፣ ባፕቲስቶች እና ሜተዲስ ቶች የራሳቸውን እምነት ለመመስረት እና ሌሎች እንደተሳሳቱ ለማረጋገጥ በእኩል በቅንአት ይጥሩም ነበር።

፲ በዚህ የቃላት ጦርነት እና በአስተያየት ሁካታ መካከል፣ ለራሴ ሁልጊዜም፥ ምን ይደረግ? እላለሁ። ከእነዚህ ቡድኖች ሁሉ የትኛዎቹ *ሠ*ትክክል ናቸው፤ ወይም ሁሉም አብረው የተሳሳቱ ናቸውን? ከእነርሱ አንዱ ትክክል ከሆነ፣ የትኛው ነው፣ እና እንዴ ትስ አውቀዋለሁ?

፲፩ በእነዚህ ሀይማኖተኛ ሰዎች ቡድኖች ፉክክር ምክንያት በጣም አስቸጋሪ በሆነው ሁኔታ እየታገልኩኝ እያለሁ፣ አንድ ቀን በያዕቆብ መልእክት ምዕራፍ አንድ አንቀፅ አምስት ውስጥ እያነበብኩ ነበር፣ እንዲህም ይል ነበር፥ *ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎ ድለው፣ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰ ጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፣ ለእርሱም ይሰጠዋል።*

፲፪ ምንም የቅዱስ መጻሕፍ ጥቅስ በዚህ ጊዜ በዚህ ጊዜ በልቤ ውስጥ ያመጣውን ሃይል ያህል በማንም ሰው ልብ ውስጥ ፈጽሞ መጥቶ አያውቅም። ይህም ወደልቤ ስሜት በሙሉ በታላቅ ሀይል የገባ ይመስል ነበር። ማንም ሰው የእግዚአብሔርን ጥበብ የሚሻ ቢኖር እኔው እንደሆንኩኝ በማወቅ፣ ይህን ደጋግሜ አሰብኩበት፤ ምን ማድረግ

፲ሠ ቅ.መ.መ. ጸብ። *፲ሀ* ቅ.መ.መ. እውነት።

እንዳለብኝ አላወቅሁምና፣ እና ካለኝ ተጨ ማሪ ጥበብ ካላገኘሁ በስተቀር፣ በምንም ማወቅ አልችልም ነበር፤ የተለያዩ ቡድ ኖች የሀይማኖት አስተማሪዎች አንድ አይ ነት የቅዱሳት መጻህፍት ምንባብን በጣም በተለያየ ሁኔታ [ሀ]ስለሚገነዘቡት፣ ጥያቄ ለመመለስ ወደ [ለ]መፅሐፍ ቅዱስ የመመካ ትን እምነትን አጥፍተውታልና።

፲፫ ከጊዜም በኋላ በጭለማ እና በግራ በመጋባት ለመቅረት ወይም ያዕቆብ እን ዳመለከተው፣ ያም እግዚአብሔርን መጠ የቅ፣ እንዳለብኝ ወሰንኩኝ። ከጊዜም በኋላ፣ ጥበብ ለሚጎድለው ጥበብ የሚሰጥ እና በልግስና ሳይነቅፍ የሚሰጥ ከሆነ [ሐ]“እግ ዚአብሔርን ለመጠየቅ” በመሞከር ውሳኔ ውስጥ ገባሁ።

፲፬ ስለዚህ፣ በዚህም እግዚአብሔርን ለመጠየቅ በወሰንኩበት መሰረት፣ ሙከራ ለማድረግ ወደ ቁጥቋጦው ውስጥ ሄድኩኝ። ጊዜውም ግሩም እና ግልፅ በሆነው በጸደይ ማለዳ በዓስራ ስመንት መቶ እና ሀያ አመተ ምህረት ነበር። በከፍተኛ ጭንቀቴ መካከል ሁሉ ድምጼን በማሰማት [ሀ]መጸለይን ገና ሞክሬው ስላልነበር፣ ይህን አይነቱን በህ ይወቴ የሞከርኩት ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር።

፲፭ ቀደም ብዬ ለመሄድ ወደመረጥኩት ስፍራ ከሄድኩ በኋላ፣ ዙሪያዬን ከተመለ ከትኩ በኋላና ብቻዬን እንደሆንኩም አየሁ፣ ተንበረከኩ እና የልቤን ፍላጎቶች ለእግዚ አብሔር መግለፅ ጀመርኩ። ይህን ማድረግ እንደጀመርኩም፣ ወዲያው በሙሉ በሚ ቋቋመኝ ሀይል ተያዝሁ፣ እና በእኔም ላይ የሚያስገርም ተፅዕኖ ኖሮት እንዳልናገርም አንደበቴን አሰረው። ጥቅጥቅ ያለ ጭለማም ዙሪያዬን ከበበኝ፣ እና ለጊዜውም በድንገት ጥፋት የተፈረደብኝ መስሎኝ ነበር።

፲፮ ነገር ግን በላዬ ላይ ከሰለጠነው የጠላት ሃይል እንዲያድነኝ ሃይሌን ሁሉ አሰባስቤ እግዚአብሔርን [ሀ]ለመጥራት እና ተስፋ ወደመቁረጥ እና ራሴንም ለጥፋት፣ ይህም ምናባዊ ጥፋት ሳይሆን ከዚህ ቀደም በየት ኛውም አካል በጭራሽ ተሰምቶኝ በማላ ውቀው አስደናቂ ሃይል ባለው ከማይታ የው አለም በሆነው አንድ ሃይል፣ አሳልፌ ለመስጠት በተዘጋጀሁበት በዚያች ቅጽ በት፣ ልክ በዚህ ታላቅ የድንጋጤ ሰአት፣ [ለ]ከፀሀይ ይልቅ የደመቀ [ሐ]የብርሀን አምድ ከራሴ በላይ ተመለከትኩ፣ በላዬም ላይ እስኪያርፍ ድረስ ይህም በዝግታ ወደ እኔ ወረደ።

፲፯ ወዲያው እንደታየም ይዞኝ ከነበረው የጠላት ሀይል በመዳን ነጻ ሆንኩ። ብር ሀኑም በእኔ ላይ ባረፈ ጊዜ ብርህነታቸ ውና [ሀ]ክብራቸው ቃላት ከሚገልጸው በላይ የሆኑ [ለ]ሁለት ሰዎች በአየር ከበላዬ ቆመው [ሐ]ተመለከትኩ። አንዱም ስሜን በመጥ ራት እና ወደሌላውም በማመልከት ተና ገረኝ—*መየምወደው [ሀ]ልጄ ይህ ነው። እር ሱን ስማው!*

፲፰ ጌታን [ሀ]የመጠየቄ ዋና አላማዬም፣ የየ ትኛው የሀይማኖት ቡድን አባል ለመሆን ለማወቅ ከቡድኖቹ ሁሉ የትኛው ትክክል እንደሆነም ለማወቅ ነበር። ስለዚህ፣ ለመ ናገር ለመቻል ራሴን ለመቆጣጠር ወዲያው እንደቻልኩም፣ ከበላዬ በብርሀን ለቆሙት ሰዎች (በዚህ ጊዜ ሁሉም የተሳሳቱ እንደ ሆኑ ምንም በልቤ ስላልገባ) የትኛው ድር ጅቶች ትክክል እንደሆነ እና የየትኛውም አባል መሆን እንደሚገባኝ ጠየቅሁኝ።

፲፱ ሁሉም [ሀ]ስህተተኞች ስለሆኑ፣ የማ ንኛዎቹም አባል እንዳልሆን ተመለሰልኝ፤ እና የሚያነጋግረኝም ሰው ሁሉም ሀይማኖ

፲፪ *ሀ* ፩ ቆሮ. ፪፡፲–፲፯።
ለ ቅ.መ.መ. መፅሐፍ ቅዱስ።
፲፫ *ሀ* ቅ.መ.መ. ጸሎት።
፲፬ *ሀ* ቅ.መ.መ. ጸሎት።
፲፯ *ሀ* ሙሴ ፩፡፳።
ለ ራዕ. ፩፡፲፯።
ሐ የሐዋ. ፳፮፡፲፫።

፲፱ *ሀ* ቅ.መ.መ. ክብር።
ለ ቅ.መ.መ. ራዕይ።
ሐ የሐዋ. ፯፡፶፭–፶፮፣ ቁላ. ፫፡፩።
ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ።
መ ማቴ. ፫፡፲፯፣ ፲፯፡፭፣ ፫፡፲፣ ፲፡፲፣ ፳፡፲፮፣ ፲፡፳፪።
ሠ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ።
፲፳ *ሀ* ት. እና ቃ. ፮፡፲፩፣ ፶፮፡፯።
፲፱ *ሀ* መዝ. ፲፡፡
ቅ.መ.መ. ክህደት—የመጀመሪያ የክርስትያን ቤተክርስትያን ክህደት።

ቶች በፊቱ አስጸያፊ እንደሆኑ፣ በእነዚህ የሚያምኑትም ሁሉ የተበከሉ እንደሆኑ፣ “በከንፈራቸው ወደ እኔ ^ይቀርባሉ፣ ሐልባ ቸው ግን ከእኔ የራቀ ነው፣ የሰው ሞትእዛ ዛት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ፣ ᵐየአም ልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደ ዋል” ብሎ ነገረኝ።

፳ የማንኛቸውም አባል እንዳልሆን እን ደገናም ከለከለኝ፤ እና በዚህ ጊዜ ልፅፋ ቸው የማልችለውን ሌሎች ብዙ ነገሮች ንም ነገረኝ። እንደገና ራሴን ለማወቅ ስጀ ምር፣ በጀርባዬ ተኝቼ ወደ ሰማይ እየተ መለከትኩ ነበር። ብርሀኑ ከሄደ በኋላ፣ ምንም ጥንካሬ አልነበረኝም፤ ነገር ግን ጥቂት ብርታት ካገኘሁ በኋላ፣ ወደ ቤት ሄድኩኝ። በቤት ማሞቂያ ምድጃ አጠገብ ተደግፌ እያለሁ፣ እናቴ ምን እንደሆንኩኝ ጠየቀችኝ። እንዲህም መለስኩኝ፣ “ምንም አታስቢ፣ ሁሉም መልካም ነው—እኔም ደህና ነኝ።” ከዚያም ለእናቴ እንዲህ አል ኳት፣ “ለራሴ ፕረስብተሪያን እውነት እን ዳልሆነ አውቄአለሁ።” ᵐጠላትም በለጋ ነት የእድሜዬ ዘመን የእርሱ የመንግስት በጥባጭ እና ረባሽ ለመሆን የተመረጥኩኝ መሆኔን ያወቀ ይመስል ነበር፤ ይህ ባይ ሆን ኖሮ የጭለማ ሀይላት ለምንስ በእኔ ላይ ይተባበሩብኝ ነበር? በህጻንነቴም፣ ለምን ^ተቃራኒዎች እና ስቃዮች በእኔ ላይ ይነ ሱብኝ ነበር?

አንዳንድ ሰባኪዎች እና ሌሎች የሀይማኖት አባሎች የመጀመሪያ ራዕይን ታሪክን አል ተቀበሉም—ስቃይ በጆሴፍ ስሚዝ ላይ ተቆለለበት—ስለራዕዩ እውነተኛነት መሰ ከረ። (አንቀፅ ፳፩–፳፮።)

፳፩ ይህን ᵐራዕይ ካየሁ ከጥቂት ቀናት በኋላ፣ ቀደም ብሎ በተጠቀሰው የሀይማኖት መነሳሳት ተሳታፊ ከነበረ ከአንድ ሜተድ ስት ሰባኪ ጋር በአጋጣሚ ተገናኘሁ፤ እና ስለሀይማኖት ርዕስ ከእርሱ ጋር ስነጋገር፣ ያየሁትን ራዕይ ታሪክ ነገርኩት። በጸባዩ በጣም ተደነቅሁኝ፤ የነገርኩትን ክብደት ሳይሰጠው፣ በንቀትም ሁሉም ከዲያብሎስ ነው፣ በእነዚህ ቀናት ^ራዕይ ወይም ሐመገ ለጥ የሚባል ነገር የለም፣ እንደዚህ አይነት ነገሮች ሁሉ ከሐዋሪያት ጋር ስለተፈጸሙ፣ እና ደግመውም አይኖሩም አለ።

፳፪ ነገር ግን ታሪኬን ስለነገርኩኝ በሀይማኖት አማኞች መካከል በእኔ ላይ የተዛባ አስተሳሰብ አነሳሳ፣ እና ሁልጊዜም የቀጠለ የታላቅ ᵐስቃይ ምክንያት ሆነ፤ እና ^ታዋቂ ያልሆንኩኝ ከአስራ አራት እና አስራ አምስት አመት መካከል የሆንኩኝ፣ እና የህይወት ጉዳዬ እንዲህ ሆኖ በአለም ላይ ምንም አስፈላጊ ያልሆንኩኝ ልጅ ነበ ርኩኝ፣ ነገር ግን ታዋቂ ሰዎች በእኔ ላይ የ ህዝቦችን አዕምሮ ለማነሳሳት፣ የሚመር ስቃይም ለመፍጠር በእኔ ላይ አተኩረው ነበር፤ እና ይህም በሁሉም ቡድኖች መካ ከል አንድ አይነት ነበር—ሁሉም እኔን በማ ስቃየት አንድ ሆነው ነበር።

፳፫ በዚያም ጊዜ በትኩረት እንዳሰላስል እና ከዚህም ጀምሮ ለብዙ ጊዜ እንዳደርገው አድርጎኛል፣ በትንሽ ከአስራ አራት አመት በላይ የሆንኩኝ ታዋቂ ያልሆንኩ ልጅ፣ እና የእለት ጉርሴን ለማግኘት በየቀኑ ስራ ለማ ግኘት የተመደብኩ፣ ለእኔ ብቁ አስፈላጊ ነት በመስጠት በጣም ታዋቂ የሆኑ ቡድኖች በክፉ ስቃይ እና ስድብ መንፈስ በውስጣ ቸው በሚፈጥር ሁኔታ በእኔ ላይ ትኩረት መስጠታቸው እንዴት የሚያስገርም ነበር። ያልተለመደም ቢሆንም ባይሆንም፣ እንደ

፲፱ *ለ* ኢሳ. ፳፱፡፲፫–፲፭፤ ሕዝ. ፴፫፡፴–፴፭።
ሐ ቅ.መ.መ. ክህደት—ታላቅ ክህደት።
መ ቲቶ ፩፡፲፭፤ ት.እና ቃ. ፴፳፡፳፱።
ሠ ፪ ጢሞ. ፫፡፭።
፳ *ሀ* ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
ለ ፪ ኔፊ ፪፡፲፭፤ ት.እና ቃ. ፶፯፡፪–፬። ቅ.መ.መ. ጭንቀት።
፳፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. የመጀመሪያው ራዕይ።
ለ ቅ.መ.መ. ራዕይ።
ሐ ቅ.መ.መ. ራዕይ።
፳፪ *ሀ* ያዕ. ፭፡፲–፲፩። ቅ.መ.መ. ማሳደድ፣ መሳደድ።
ለ ፩ ሳሙ. ፲፯፡፲፯፤ አልማ ፴፯፡፴፭።

ዚህም ነበረ፣ እና ለእኔም ታላቅ ሀዘን ሁል ጊዜም የፈጠረብኝ ነበር።

፳፭ ነገር ግን ራዕይ እንዳየሁ በምንም ቢሆን እውነት ነው። አሁንም ሳስብበት፣ በንጉስ አግሪጳ ፊት "እንደተከራከረው፣ እና ብርሀንን ሲያይ ስለነበረው ራዕይ ታሪክ እንደነገረው ᵃጳውሎስ አይነት ይሰማኝ ነበር፤ ነገር ግን ያመኑት ብዙ አልነበሩም፤ አንዳንዶችም እርሱ ሀሰተኛ ነው፣ ሌሎ ችም እርሱ ያበደ ነው ብለውም ነበር፤ እና ያፌዙበትም ይሰድቡትም ነበር። ይህ ሁሉ ግን ራዕዩ እንደነበረው እውነትን አላጠፋ ውም። ራዕይ አይቷል፣ ማየቱንም አው ቋል፣ እና ከሰማይ በታች ያሉት ስቃዮች ሁሉ ሊለውጡት አይችሉም፤ እና እስከሚ ሞት ድረስ ቢያሰቃዩትም፣ ማየቱን ያው ቀው ነበር፣ እና ብርሀንን እንዳየ እና ያና ገረውን ድምፅ እንደሰማ እስከመጨረሻው እስትንፋሱ ድረስ ያውቀዋል፣ እና አለም ሁሉ ከዚህ ሌላ እንዲያስብ ወይም እንዲ ያምን ሊያደርጉት አይችሉም።

፳፮ ለእኔም እንዲሁ ነበር። ብርሀንን በእ ውነትም አይቼ ነበር፣ እና በብርሀኑ መካከ ልም "ሁለት ሰዎችን አየሁ፣ እና እነርሱም በእውነት አነጋገሩኝ፤ እና ምንም እንኳን ራዕይ አይቻለሁ በማለቴ ብጠላና ብሰቃ ይም፣ ይህ ግን እውነት ነበር፤ እና ይህን በማለቴ እነርሱ ሲያሰቃዩኝ፣ ሲሰድቡኝና፣ ሁሉንም አይነት ክፉ ነገሮች በእኔ ላይ ሲያ ደርጉብኝ፣ በልቤም ይህን እንድል ተመ ርቼ ነበር፡ እውነትን በመናገሬ ለምን ታሰ ቃዩኛላችሁ? በእውነትም ራዕይን አይቻ ለሁ፤ እና እግዚአብሔርን እቋቋም ዘንድ ማን ነኝ፣ ወይም ለምን አለም በእርግጥ ያየ ሁትን እንድክደው ለማድረግ ያስባል? ራዕ ይን አይቻለሁ፣ አውቀዋለሁ፣ እና እግዚ አብሔር እንደሚያውቀውም አውቃለሁ፣ እና ᵃልክደውም አልችልም፣ እና ይህን ላደርግም አልሞክርም፣ ይህን በማድረግ እግዚአብሔርን እንደሚያስቀይምና ፍርድ በላዬ እንደሚመጣብኝ አውቃለሁና።

፳፯ የሀይማኖት አለምን በሚመለከት—ከማንኛቸው ጋር አባል መሆኑ የእኔ ሀላፊ ነት አልነበረም፣ ነገር ግን ተጨማሪ መመ ሪያ እስካገኝ ድረስ እንደነበርኩትም መቀ ጠል እንዳለብኝ በማወቅ አዕምሮዬ ረክቶ ነበር። የያዕቆብ "ምስክር እውነት እንደሆ ነም አወቅሁኝ—ጥበብ የሌለው ሰው እግ ዚአብሔርን መጠየቅ ይችላል፣ እና አይ ነቀፍም።

ምሮኒ ጆሴፍ ስሚዝን ጎበኘው—የጆሴፍ ስም ለበጎም ሆነ ለክፉም በህዝቦች መካከል ይታወቃል—ሞሮኒ ስለመፅሐፈ ሞርሞ ንና ስለሚመጣው የጌታ ፍርድ ነገረው እና ቅዱስ መጻህፍትንም ጠቀሰ—የወርቅ ሰሌ ዳው ስውር ስፍራ ተገለጸ—ሞሮኒ የነቢ ዩን ትምህርት ቀጠለ። (አንቀፅ ፳፫–፴፩።)

፳፰ የእለት ህይወቴ ስራዬን እስከ መስከ ረም ሀያ አንደኛው ቀን፣ አንድ ሺህ ስምንት መቶ ሀያ ሶስት (እ.አ.አ.) ድረስ ቀጠልኩ፣ በዚህም ጊዜ ሁሉ፣ ራዕይ እንዳየሁ ማረ ጋግጥን ስለቀጠልኩኝ፣ በሁሉም አይነት ሰዎች፣ ሀይማኖታዊም ይሁን ሀይማኖት በሌላቸው፣ ብዙ ተሰቃየሁኝ።

፳፱ ራዕይ ካየሁበት እና በአስራ ስምንት መቶ ሀያ ሶስት አመተ ምህረት መካከል በነ በረው ጊዜ—በዚያ ጊዜ ከነበሩት ከማና ቸውም የሀይማኖት ድርጅቶች አባል እን ዳልሆንም ስለተከለከልኩኝ፣ እና በጨቅ ላዎቼ እድሜዬ ላይ ስለነበርኩኝ እና ግራ የተጋባሁ እንደሆንኩ የሚያስቡም ቢሆን በትክክለኛውና በመልካም የፍቅር ስሜት እንደገና ከስህተቴ ሊመልሱኝ በሚገባ ቸው ባልንጀሮቼ ሊሆኑና በርህራሄም ሊመ ለከቱኝ በሚገባቸው ስደት የደረሰብኝ—በሁሉም አይነት ፈተናዎች ተፈተንኩኝ፤ እና ከሁሉም አይነት ህብረተሰብ ጋር በመ

፳፩ *ሀ* የሐዋ. ፳፮።
ለ ቅ.መ.መ. ጳውሎስ።
፳፭ *ሀ* ጆ.ስ.—ታ. ፩፡ ፲፯።
ለ ቅ.መ.መ. መበርታት፣ ብርቱነት፤ ቅንነት።
፳፮ *ሀ* ያዕ. ፩፡ ፭–፮።

ቀላቀልም፣ በብዙ ጊዜም የሞኝ ስህተቶ ችን ሰራሁ፣ እና የወጣትነትን ደካማነትንና የሰው ፍጥረት ፍጹም ያለመሆንን አሳየሁ፣ ይህም በእግዚአብሔር አስተያየት በሚያ ስቀይሙ ወደተለያዩ ᵐፈተናዎች ስለተመ ራሁ ጸጸት ይሰማኛል። ይህን በመናዘዜ፣ ማንም በምንም ታላቅ እና ክፉ ኃጢአቶ ችን የሰራሁ አይምሰለው። እንደዚህ አይነት ነገር የመፈጸም ዝንባሌም አልነበረኝም። ነገር ግን እኔ እንደነበርኩት ከእግዚአብሔር ᵃየተጠራ ሰው እንዲኖረው በማይገባ አይ ነት ጸባዮች፣ በቅብጠት፣ እና አንዳንዴም ከሚደሰቱ ሰዎች ጋር መገናኘት፣ እና በሌ ሎችም ጥፋተኛ ነበርኩኝ። ነገር ግን ወጣ ትነቴን በሚያስታውሱት እና በሀገራዊ ደስ ተኛ ጸባዬን በሚያውቁት ዘንድ ይህ አስገ ራሚ ላይሆን ይችላል።

፳፭ በእነዚህ ነገሮች ምክንያት፣ በደካማነቴ እና ፍጹም ባለመሆኔ እንደ ተኮነንኩኝ ይሰማኝ ነበር፤ ከላይ እንደተ ጠቀሰውም በመስከረም ሀያ አንድ ቀን፣ በምሽት ወደመኝታዬ ከገባሁ በኋላ፣ ወደ ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር ለኃጢአቶቼ እና ለጥፋቶቼ ይቅርታ በመጠየቅ፣ እና በፊቱ የት እንዳለሁ እና ምን ላይ እንደቆ ምኩኝ አውቅ ዘንድ እንዲገለጥልኝ ᵐእጸ ልይ እና አመልክ ነበር፤ ከዚህ በፊት እንደ ነበረኝ መለኮታዊ መገለጥን ለማግኘት ሙሉ እምነት ነበረኝ።

፴ እግዚአብሔርን በመጥራት ላይ ባለሁ በት ጊዜ፣ ብርሃን በክፍሌ ውስጥ ሲመጣ ተመለከትኩ፤ ብርሃኑም ከቀትር ፀሐይ እስ ኪበልጥ ድረስ መጨመሩን ቀጠለ፤ ወዲያ ውኑም አንድ ᵐሰው በአልጋዬ አጠገብ እግሩ መሬት ሳይነካ በአየር ላይ ቆሞ ተገለጠልኝ።

፴፩ በጣም ያሸበረቀ ነጭ ካባ ለብሶ ነበር። ᵐንጣቱም ምድራዊ ከሆኑ ካየኋቸው ነገሮች በሙሉ የበለጠ ነበር፤ ማንኛውም ምድ ራዊ ነገር እንደዚህ እጅግ ነጭና ደማቅ መሆን ይችላል ብዬ አላምንም። እጆቹ፣ እናም ደግሞ ክንዶቹ ከአንጓው ትንሽ ከፍ ብሎ በልብስ አልተሸፈኑም ነበር፤ እግ ሮቹም ደግሞ እንዲሁ ከቁርጭምጭሚቱ በላይ በልብስ አልተሸፈኑም ነበር። ራሱና አንገቱም የተገለጡ ነበሩ። ካባው በተገ ለጠ ጊዜ ደረቱን ማየት እችል ስለነበር፣ ከካባው በቀር ሌላ ልብስ እንዳልነበረው ለማወቅ ችዬ ነበር።

፴፪ እጅግም የነጣው ካባው ብቻ አልነበ ረም፣ ነገር ግን መላ ሰውነቱ መግለፅ ከሚ ቻለው በላይ ᵐብሩህ ነበር፣ እንዲሁም ፊቱ በእውነት ልክ እንደ ᵃመብረቅ ነበር። ክፍሉ እጅግ ብርሃን ነበር፣ ነገር ግን ልክ በእርሱ ዙሪያ እንደነበረው በጣም የደመቀ አልነበ ረም። በመጀመሪያም ወደ እርሱ በተመለ ከትኩ ጊዜ ᵃፈርቼ ነበር፣ ነገር ግን ፍርሃቱ ወዲያው ለቀቀኝ።

፴፫ ᵐበስሜ ጠራኝ፣ እናም እርሱ ከእግዚ አብሔር ዘንድ ወደ እኔ የተላከ መልዕክተኛ እንደሆነና ስሙም ሞሮኒ እንደሆነ፣ እግዚ አብሔርም ለእኔ የምሰራው ስራ እንደነበ ረው፣ እናም ስሜም በሁሉም ሀገሮች፣ ነገ ዶች፣ ቋንቋዎችና ህዝብ መካከል በመልካ ምና በጥፋት እንደሚነሳ፣ ወይም በሁሉም ህዝብ መካከል መልካምና መጥፎ እንደሚ ባልልኝ ነገረኝ።

፴፬ እርሱ ቀደም ያሉትን የዚህ አህጉር ነዋሪዎች ታሪክ እና እነርሱ የመጡበትን ምንጭ ከየት እንደሆነ የሚናገር ᵐበወርቅ ሰሌዳዎች ላይ ተፅፎ የተቀበረ ᵃመጽሐፍ እንዳለም ተናገረ። ለጥንት ነዋሪዎች በአ ዳኙ የተሰጠውን የዘለዓለማዊውን ወንጌል

፳፯ ᵐ ቅ.መ.መ. መፈተን፣ ፈተና።
ᵃ ቅ.መ.መ. ጥሪ፣ በእግዚአብ ሔር መጠራት፣ የተጠራበት።
፳፱ ᵐ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
፴ ᵐ ቅ.መ.መ. መላእክት፤ ሞሮኒ፣ የሞርሞን ልጅ።
፴፩ ᵐ የሐዋ. ፲፡፴፤ ፩ ኔፊ ፳፡፲፤ ፲፫፡፳፭–፳፮፤ ፲ ኔፊ ፲፡፲–፳፡፳፤ ፴፪ ᵐ ፲ ኔፊ ፲፡፲–፳፡፳፤ ቅ.መ.መ. ክብር።
ᵃ ዘፀአ. ፴፡፲፡፳–፴፭፤ ሐሌ. ፭፡፴፤ ፴፮፤ ት. እና ቃ. ፲፣፲፡፲።
ᵐ ዘፀአ. ፲፡፲፤ ፲፡፲–፳፡ ፲፱፡፲–፳፡ ፲ ኔፊ ፲፡፲–፳፡ ፴፫ ᵐ ዘፀአ. ፴፣፲፡፲፪፣ ፲፯፤ ኢሳ. ፴፭፡፲–፴፡ ፴፬ ᵐ ቅ.መ.መ. የወርቅ ሰሌዳዎች። ᵃ ቅ.መ.መ. መፅሐፈ ሞርሞን።

ሐሙሉነትም በውስጡ እንደያዘም ደግሞ ተናገረ፤

፳፩ ደግሞ ከሰሌዳዎቹ ጋር የተቀበሩ ሁለት ድንጋዮች በብር ቅስት ውስጥ ነበሩ—እናም እነዚህ ድንጋዮች ᵐከደረት ኪስ ታስረው፣ ᵃኡሪምና ቱሚም ከሚባለው የተሰሩ ናቸው፤ እናም የእነዚህ ድንጋዮች ባለቤትና ተጠቃሚ በጥንት ወይም በድሮ ጊዜ ᵃባለራዕይ የሚባሉት ናቸው፤ እናም እግዚአብሔር መጽሐፉን ለመተርጎም ዓላማ እነሱን አዘጋጅቷቸዋል።

፳፪ እነዚህን ነገሮች ከነገረኝ በኋላ ᵐከብሉይ ኪዳን ትንቢቶችን መጥቀስ ጀመረ። መጀመሪያ የጠቀሰው የሚልክያስ መፅሐፍ ᵃምዕራፍ ሶስትን ክፍል ነበር፤ ደግሞም የዚያን ትንቢት አራተኛ ወይም የመጨረሻ ምዕራፍ፣ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚነበብበት በትንሽ ቀይሮ ጠቀሰ። የመጀመሪያውን አንቀጽ በመፅሐፎቹ እንደሚነበበው ከመጥቀስ ፈንታ፣ እንዲህ ጠቀሰው፥

፳፫ እነሆም፣ እንደ ምድጃ እሳት ᵐየሚነድ ᵃቀን ይመጣል፤ እናም ትዕቢተኞች ሁሉ፣ አዎን፣ እናም ኃጢአትን የሚሰሩ ሁሉ እንደ ሐገለባ ይቃጠላሉ፤ የሚመጡትም ያቃጥሏቸዋል፣ አለ የሰራዊት ጌታ፣ ሥርንና ቅርንጫፍንም አይተውላቸውም።

፳፬ ደግሞም አምስተኛውን አንቀፅ እንዲህ ጠቀሰ፥ እነሆ ታላቁና የሚያስፈራው የጌታ ቀን ከመምጣቱ በፊት በነቢዩ ᵐኤሊያስ እጅ ᵃክህነትን እገልጥላችኋለው።

፳፭ የሚቀጥለውንም አንቀጽ በልዩነት ጠቀሰው፥ እናም ለአባቶች የተገባውን ᵐየተሰፋ ቃል በልጆች ልብ ይተክላል፣ እናም የልጆቹንም ልብ ወደ አባቶቻቸው ᵃይመልሳል። እንዲህ ባይሆን ኖሮ፣ መላው ምድር በምጽአቱ ይጠፋ ነበር።

፳ በእነዚህም ተጨማሪ፣ የኢሳይያስ ምዕራፍ አስራ አንድ በዚህ ያሉት ሊፈጸሙ ተቃርበዋል በማለት ጠቀሰ። የሐዋርያት ስራ ምዕራፍ ሶስት፣ ሀያ ሁለት እና ሀያ ሶስት አንቀፅን በአዲስ ኪዳን ውስጥ በትክክል እንደሚገኙት ጠቀሰ። ᵐነቢዩም ክርስቶስ ነበር፤ ነገር ግን “ድምጹን የማይሰሙ ከሕዝብ ᵃተለይተው ይጠፋሉ” የተባለበት ቀን ገና አልመጣም፣ ግን ወዲያው ይመጣል አለ።

፳፮ ᵐየኢዩኤልን ሁለተኛ ምዕራፍ ከአንቀፅ ሀያ ስምንት እስከ መጨረሻውም ጠቀሰ። ደግሞም ይህ ገና እንዳልተፈጸመ፣ ግን ወዲያውም እንደሚሆን ተናገረ። በተጨማሪም ᵃየአህዛብ ሙላት ወዲያው እንደሚመጣም ተናገረ። ከቅዱሳት መጻህፍት ብዙ ምንባብን ጠቀሰ፣ እና በዚህ ሊጠቀሱ የማይችሉ ብዙ ማብራሪያዎችንም ሰጠ።

፳፯ ደግሞም፣ እርሱ የተናገረኝን ሰሌዳዎች ሳገኝ—እነርሱን የምወስድበት ትክክለኛው ጊዜ ገና አልተፈጸመምና—እኔ ማሳየት እንዳለብኝ ከምታዘዘው በቀር የደረት ኪሱን ከኡሪምና ቱሚም ጋር ለማንም ሰው ማሳየት እንደሌለብኝና ካደረግሁ ግን መጥፋት እንዳለብኝ ተናገረኝ። እርሱ ከእኔ ጋር ስለሰሌዳዎቹ በሚነጋገርበት ጊዜ፣ ሰሌዳዎቹ የተቀበሩበትን ስፍራ ማየት እንድችል ራዕይ ᵐለአዕምሮዬ ተገለፀ፣ እናም ስፍራ

፳፩ሐ ቅ.መ.መ. የወንጌል ዳግም መመለስ።

፳፫ ሀ ዘሌዋ. ፳፡፳። ቅ.መ.መ. የደረት ኪስ።
ለ ዘፀአ. ፳፰፡፡ ቅ.መ.መ. ኡሪም እና ቱሚም።
ሐ ቅ.መ.መ. ባለራዕይ።

፳፯ ሀ ቅ.መ.መ. ብሉይ ኪዳን።
ለ ቅ.መ.መ. ሚልክያስ።

፳፯ ሀ ፫ ኔፊ ፳፭፤ ት. እና ቃ. ፳፡፩፡፳፫–፳፭። ቅ.መ.መ. ምድር—ምድርን ማፅዳት፤ አለም—የአለም መጨረሻ።
ለ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
ሐ ናሆ ፩፡፳–፲፣ ፩ ኔፊ ፳፪፡፲፣ ፳፫፣ ፪ ኔፊ ፳፭፡፲–፲፮፤ ት. እና ቃ. ፳፱፡፱። ፳፭ ሀ ት. እና ቃ. ፳፯፡፱፤ ፻፲፡፲፣ ፲፫–፲፮። ቅ.መ.መ. ኤልያስ።
ለ ቅ.መ.መ. ክህነት፤ የክህነት ቁልፎች።

፳፱ ሀ ገላ. ፫፡፳፣ ፲፱። ለ ቅ.መ.መ. ለሙታን ደህንነት፤ የትውልድ ሐረግ።

፳ ሀ ዘዳግ. ፲፰፡፲፭–፲፱።
ለ ፫ ኔፊ ፳፡፳፣ ፳፩፡፳።

፳፩ ሀ የሐዋ. ፪፡፲፯–፳፩።
ለ ሮሜ ፲፩፡፲፩–፳፭፤ ት. እና ቃ. ፹፡፳፡፹፭። ቅ.መ.መ. አህዛቦች።

፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. አዕምሮ።

ውንም እንደገና ስጎበኘው በግልፅና በጉልህ አወቅሁት።

፶፫ ከዚህ ንግግርም በኋላ፣ ብርሃን በክ ፍሉ ውስጥ ባናገረኝ ሰው ዙሪያ በፍጥነት መሰብሰብ ሲጀምር አየሁ፣ እናም ከእርሱ ዙሪያ በቀር ክፍሉ እንደገና እስኪጨልም ድረስ እንዲህም ማድረግ ቀጠለ፤ ወዲያ ውም ስመለከት መተላለፊያ ቀጥታ ወደ ሰማይ የተከፈተ መሰለኝ፣ እና እርሱ እስ ኪጠፋ ድረስ ወደላይ አረገ፣ እናም ክፍሉ ይህ ሰማያዊ ብርሃን ከመታየቱ በፊት እን ደነበረው ሆነ።

፶፬ እኔም ተኝቼ በዚህ እንግዳ ዕይታ በጥንቃቄ እያሰብኩ፣ እናም ይህ እንግ ዳው መልዕክተኛ በነገረኝ በጣም እየተ ደነቅሁ ነበር፤ በሃሳቤ [a]ሳወጣና ሳወርድ፣ ክፍሌ እንደገና እየደመቀ መምጣቱን በድ ንገት ተመለከትኩ፣ እናም በቅፅበት ያው የሰማይ መልዕክተኛ በድጋሚ አልጋዬ አጠ ገብ መሆኑን ተመለከትኩ።

፶፭ እርሱም መናገር ጀመረ፣ እናም እን ደገና በመጀመሪያ ጉብኝቱ ያደረጋቸውን አንድ አይነት ነገሮች ምንም ሳይለውጥ ተናገረ፤ ይህንን ካደረገ በኋላ ታላቅ ፍርድ በምድር ላይ ከታላቁ ጥፋት ጋር በረሃብ፣ በሰይፍ እና በቸነፈር እንደሚመጣ፤ እናም እነዚህ አሳዛኝ ፍርዶች በምድር ላይ በዚህ ትውልድ እንደሚመጡ ገለፀልኝ። እነዚ ህን ነገሮች ከነገረኝ በኋላ ልክ እንደ በፊቱ በድጋሚ አረገ።

፶፮ በዚህ ጊዜ በአዕምሮዬ የተቀረፁት በጣም ጥልቅ ነገሮች ስለነበሩ፣ እንቅልፍ ከዐይኖቼ ጠፋ፣ እናም ባየሁትና በሰማሁት በመደነቅ ተሞላሁ። ነገር ግን ይገርመኝ የነ በረው ነገር በድጋሚ ያንን መልዕክተኛ በአ ልጋዬ በኩል ሳየው፣ እናም ያንኑ የበፊቱን ነገሮች እንደገና ሲደግመው ስሰማ ነበር፤ እናም ማስጠንቀቂያ ሲጨምርልኝ ነበር፣ (የአባቴ ቤተሰቦች ድሃ በመሆናቸው ምክን ያት) [b]ሰይጣን ሀብታም ለመሆን ዓላማ ሰሌ ዳዎቹን ለማግኘት እንዳገኝ [c]ሊፈትነኝ እን ደሚሞክር በመንገር ተጨማሪ ማስጠንቀቂ ያን ሰጠኝ። እርሱም ይኸውም ጌታን ለማ ሞገስ ካልሆነ በስተቀር ሰሌዳዎቹን በማግ ኘቴ ሌላ አእምሮዬን [d]የማያነሳሳ ነገር እን ዳይኖረኝ፣ እናም የእርሱን መንግስት ከመ ገንባት ሌላ በማንኛውም ነገር ተፅዕኖ እን ዳይኖርብኝ በማለት ከለከለኝ፤ አለበለዚያ እነዚህን ለማግኘት አልችልም።

፶፯ ከዚህ ከሦስተኛው ጉብኝት በኋላ፣ ልክ እንደበፊቱ በድጋሚ ወደ ሰማይ አረገ፣ እናም አሁን ስለአጋጠመኝ እንግዳ ነገር በድጋሚ እንዳሰላስል ተተውኩ፤ ልክ የሰ ማዩ መልዕክተኛ ለሦስተኛ ጊዜ እኔ ከነበ ርኩበት ወደ ሰማይ ሲያርግ፣ ዶሮ ጮኸ፣ እናም እየነጋ መሆኑን ተገነዘብኩ፣ ስለዚህ ንግግራችንም ያን ምሽት በሙሉ የያዘ እን ደነበር ተረዳሁ።

፶፰ ከጥቂት ጊዜም በኋላ ከመኝታዬ ተነ ሳሁ፤ እናም እንደተለመደው፣ ለቀኑ አስ ፈላጊ ወደ ሆነው ስራ ሄድኩ፤ ነገር ግን በሌላ ጊዜ እንደምሰራው ስሞክር፣ ኃይ ልን በማጣቴ ያንንም ለመስራት ፍፁም አላ ስቻለኝም። ከእኔ ጋር ሲሰራ የነበረው አባቴ በእኔ በኩል አንድ ችግር እንዳለ ተገነዘበ፣ እናም ወደ ቤት እንድሄድ ተናገረኝ። በፍ ላጎት ወደ ቤት ለመሄድ ጀመርኩ፤ ነገር ግን እኛ የነበርንበትን የሜዳ አጥር ለማቋረጥ ስሞክር ብርታቴን በሙሉ አጣሁ፣ እናም አቅቶኝ በመሬት ላይ ወደቅሁ፣ እናም ለተ ወሰነ ጊዜ አዕምሮዬን ስቼ ነበር።

፶፱ የመጀመሪያው የማስታውሰው ነገር አንድ ድምፅ ወደ እኔ ተናግሮ፣ በስሜም ሲጠራኝ ነበር። ተመለከትኩ፣ እናም የፊ ተኛው መልዕክተኛ ልክ እንደበፊቱ በብር ሃን ተከቦ በአናቴ በኩል ቆሞ አየሁ። እናም እርሱ ባለፈው ምሽት ለእኔ የተናገረውን ሁሉ እንደገና ተናገረ፣ እናም ወደ [e]አባቴ በመሄድ ስለራዕዩና ስለተቀበልኩት ትዕዛ ዛት እንድነግረው አዘዘኝ።

---

[a] ሀ ቅ.መ.መ. ማሰላሰል።
[b] ሀ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
[c] ለ ቅ.መ.መ. መፈተን፣ ፈተና።
[d] ሐ ት. እና ቃ. ፤፳፭፤ ፴፯።
[e] ሀ ቅ.መ.መ. ስሚዝ፣ ጆሴፍ ቀዳማዊ።

፱ እኔም ተቀበልኩ፤ በሜዳው ወደአለው አባቴም ተመለስኩ እናም ሁሉንም ነገር ለእርሱ ነገርኩት። እርሱም ከእግዚአብሔር ነው ብሎ መለሰልኝ፣ እናም በመልዕክተኛው የታዘዝኩትን እንድሄድና እንዳደርግ ነገረኝ። ከሜዳው ሄድኩኝ፣ እናም መልዕክተኛው ሰሌዳዎቹ ተቀምጠዋል ብሎ ወደ ነገረኝ ስፍራ ሄድኩኝ፤ እና ያንን በተመለከተ ግልፅ ራዕይ ስለነበረኝ፣ ወደስፍራው እንደደረስኩ ወዲያው አወቅሁት።

፱፩ በኒውዮርክ በማንቸስተር ኦንታሪዮ መንደር አጠገብ አንድ ትልቅ [1]ኮረብታ ቆሟል፣ እናም በአቅራቢያው ካሉት ከሌሎች ሁሉ ይበልጣል። በኮረብታው በስተ ምዕራብ በኩል ከጫፉ ራቅ ሳይል፣ በትልቁ ድንጋይ ስር ሰሌዳዎቹ በድንጋይ ሳጥን ተቀብረዋል። ይህም ድንጋይ በላይ በኩልና ከመሀሉ ወፍራምና ክብ ነበር፣ እና ወደጠርዙም በኩል ቀጭን ነበር፣ ስለዚህ የመካከለኛው ክፍሉ ከመሬት በላይ ከፍ ብሎ ይታይ ነበር፤ ነገር ግን ጠርዞቹ በሙሉ በመሬቱ ተሸፍነው ነበር።

፱፪ ከመሬት ከቆፈርኩም በኋላ፣ ከድንጋዩ ጠርዝ ላይ የተጣበቀ ለማንሻነት የሚጠቅም ዱላ አገኘሁ፣ እናም በትንሽ ጉልበት አነሳሁት። ወደ ውስጥም ተመለከትኩ፣ እናም መልዕክተኛው እንደገለፀው በእርግጥ [2]ሰሌዳዎቹን፣ [3]ኡሪምና ቱሚም እናም [4]የደረት ኪሱን ተመለከትኩ። በውስጡ የተቀመጡበት ሳጥንም የተሰራው ሲሚንቶ በሚመስል በተጣበቁ በተነባበሩ ድንጋዮች ነበር። ከሳጥኑ በታች በኩል ሁለት ድንጋዮች ጎን ለጎን ተቀምጠው ነበር፣ እናም በእነዚህ ድንጋዮች ላይም ሰሌዳዎችና ሌሎች ነገሮች ተቀምጠውባቸው ነበር።

፱፫ እኔ እነርሱን ለማውጣት ሞከርኩ፣ ነገር ግን በመልዕክተኛው ተከለከልኩ፣ እናም እንደገና የነሱ ማውጫ ጊዜ ገና እንዳልደረሰ፣ ከዚያም ጊዜም እስከ አራት አመት ድረስም ጊዜው እንደማይመጣም ነገረኝ፤ ነገር ግን እርሱ ልክ በአንድ አመት ጊዜ ወደዚያ ስፍራ መምጣት እንዳለብኝ ነገረኝ፣ እናም እርሱ እዚያ ከእኔ ጋር ለመገናኘት እንደሚመጣ፣ እና ሰሌዳዎቹ የሚወሰዱበት ጊዜ እስከሚመጣ ይህን ማድረግ መቀጠል እንዳለብኝ ተናገረኝ።

፱፬ በመሰረቱም እንደታዘዝኩት፣ በየአመቱ መጨረሻ ሄድኩኝ፣ እናም በእያንዳንዱ ጊዜም ያንኑ መልዕክተኛ እዚያ አገኘሁት፣ እናም በእያንዳንዱ ንግግራችን ጌታ ምን እንደሚያደርግ በተመለከተ፣ እና እንዴትና በምን አይነት ሁኔታ የእርሱ [5]መንግስት በመጨረሻው ቀን እንደሚመራ መመሪያና እውቀት ከእርሱ እቀበል ነበር።

ጆሴፍ ስሚዝ ኤማ ሐልስን አገባ—የወርቅ ሰሌዳዎችን ከሞሮኒ ተቀበለ እና አንዳንድ ፊደሎችን ተረጎመ—ማርቲን ሀሪስ የፊደሎችን ትርጉም፣ "የታተመ መፅሐፍ ለማንበብ አልችልም" ላለው ፕሮፌሰር አንቶን አሳየ። (አንቀፅ ፱፭–፰፰።)

፱፭ የአባቴ አለማዊ ሁኔታ የተወሰነ ስለነበረ፣ እድሎች ባጋጠሙን ቁጥር በእጆቻችን በመስራት እንደ ቀን ሰራተኞች በመቀጠር መስራት ነበረብን። አንዳንዴ እቤት ነን፣ እና አንዳንዴም በውጪ ነን፣ እና በየጊዜው በመስራትም የሚመች መጠነኛ ኑሮ እንዲኖረን ችለናል።

፱፮ በ፲፰፻፳፭ ዓመተ ምህረት (እ.አ.አ.) የአባቴ ቤተሰብ የታላቅ ወንድሜ፣ [6]አልቪን፣ የሞተበት ስቃይ አጋጠማቸው። በጥቅምት ወር፣ ፲፰፻፳፭ (እ.አ.አ.)፣ በኒውዮርክ ስቴት፣ ቻነንጎ ወረዳ በሚኖረው ስሙ ጆዛያ ስቶል በተባለ ሽማግሌ ሰው ተቀጠርኩ። በስፓኒያን በሀርመኒ፣ ሰስኮሀና ወረዳ ፔንስልቬንያ ውስጥ የብር የማእድን

[1] ፱፩ ሆ ቅ.መ.መ. የከሞራ ኮረብታ።
[2] ፱፪ ሆ ሞር. ፮፡፮።
[3] ቅ.መ.መ. የወርቅ ሰሌዳዎች።
[4] ለ ቅ.መ.መ. ኡሪም እና ቱሚም።
[5] ሐ ቅ.መ.መ. የደረት ኪስ።
[6] ፱፩ ሆ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር መንግስት ወይም መንግስተ ሰማያት።
[7] ፱፮ ሆ ት. እና ቃ. ፲፴፯፡፩–፰።

ጉድጓድ እንደተከፈተ ሰምቶ ነበር፤ እና ይህን የማዕድን ጉድጓድ ለማግኘት የሚቻል ከሆነ እኔን ከመቅጠሩ በፊት ይቆፍር ነበር። ከእርሱ ጋር ለመኖር ከሄድኩኝ በኋላ፣ ከሌሎቹ ሰራተኞቹ ጋር በብር የማዕደን ጉድጓድ ውስጥ እንድቆፍር ወሰደኝ፣ በምናደርገው ውጤታማ ሳንሆን፣ ለአንድ ወር በሚሆንም በዚህም እሰራ ነበር፣ እና በመጨረሻም ይህን ለመቆፈር እንዲያቆም ሽማግሌውን አንዲስማማ አደረግሁኝ። በዚህም እኔን የገንዘብ ቆፋሪ ነው የሚለው የተሰራጨ ታሪክ ተነሳ።

፶፯ እንደዚህ በተቀጠርኩበት ጊዜም፣ ከዚያው ስፍራ አቶ አይዛክ ሔልስ ጋር አብረን እንድኖር ተደርጌ ነበር፣ እዚያም ነበር ባለቤቴን (ሴት ልጁን) ᵐኤማ ሔልስን ለመጀመሪያ ጊዜ ያየኋት። በጥር ፲፰፣ ፲፰፻፳፯ (እ.አ.አ.)፣ አቶ ስቶልን ለማገልገል እንደተቀጠርኩ ተጋባን።

፶፰ ራዕይን አይቼ ነበር በማለት በማረጋገጥ መናገሬን በመቀጠሌ፣ ᵐስቃይ ተከተለኝ፣ እና የባለቤቴ አባት ቤተሰብም ጋብቻችንን በጣም ተቃውመውት ነበር። ስለዚህ፣ እርሷን ወደ ሌላ ስፍራ መውሰድ ያስፈልገኝ ነበረ፤ ስለዚህ፣ ሄድን እና በሳውዝ ቤይንብርጅ፣ በቸናንጎ ወረዳ ኒው ዮርክ፣ በዳኛ ታርቢል ቤት ውስጥ ተጋባን። ከጋብቻችን በኋላ ወዲያውም፣ አቶ ስቶልን ትቼ ወደ አባቴ ተመለስኩኝ፣ እና ለጊዜውም አብሬው አረስኩኝ።

፶፱ ከጊዜ በኋላ ሰሌዳውን፣ ኡሪምና ቱሚምን፣ እና የደረት ኪስን የምቀበልበት ጊዜ ደረሰ። በመስከረም ሀያ ሁለተኛው ቀን፣ አንድ ሺህ ስምንት መቶ ሀያ ሰባት ዓመተ ምህረት፣ እንደለመድኩት በአመቱ መጨረሻ ላይ ሰሌዳዎቹ ወደተቀበሩበት ስፍራ ሄጄ፣ ያው መላዕክተኛ ሰሌዳዎችን እንዲህ ከሚል ከትእዛዝ ጋር ሰጠኝ፥ ለእነርሱም ሀላፊነት አለኝ፤ ᵐበቸልተኝነት ወይም በዝንጉነት ምክንያት ቢጠፉብኝ፣ ከህይወት ተለይቼ እንደምቆረጥ፣ ነገር ግን መዕክተኛው መልሶ እስከሚጠይቅባቸው ድረስ ተግቼ ብጠብቃቸው፣ ᵃይጠበቃሉ።

፰ እነዚህን በደንብ እንድጠብቃቸው ለምን እንደዚህ አይነት ጥብቅ ትእዛዝ እንደተቀበልኩኝ፣ እና ለምን መልእክተኛው በእጆቼ አስፈላጊ የሆኑትን ከፈጸምኩኝ በኋላ መልሶ እንደሚወስዳቸው እንደነገረኝ ወዲያው አወቅሁኝ። እነዚህ እንዳሉኝ ወዲያው ሲታወቅ፣ ወዲያኑ እነዚህን ከእኔ ለመውሰድ ብርቱ ተፅዕኖ ተፈጥሮ ነበር። ሊፈጠር የሚቻለው እያንዳንዱ እቅድ ሁሉ ለዚህ አላማ ተሞክሮ ነበር። ስቃዩም ከቀድሞው በላይ የከፋ እና ሀይለኛም ሆነ፣ እና ብዙዎችም የሚቻል ከሆነ እነዚህን ከእኔ ለመውሰድ በንቃት ይጠብቁ ነበር ነገር ግን በእግዚአብሔር ጥበብ፣ በእጆቼ የተጠበቁ ብኝን በእነርሱ እስክፈፅም ድረስ፣ በእጆቼ በደህንነት ቆዩ። በታቀደው መሰረት መልእክተኛው ሊወስዳቸው ሲመጣ፣ እነሱንም መልሼ ሰጠሁት፤ እና እስካሁን እስከ ግንቦት ሁለት ቀን፣ አንድ ሺህ ስምንት መቶ ሰላሳ ስምንት አመተ ምህረት ደረስ በእርሱ ጥበቃ ስር ናቸው።

፰፩ ትርምሱ ግን አሁንም ቀጥሏል፣ እና አሉባልታም በአንድ ሺህ ምላሶቿ ስለአባቴ ቤተሰቦችና ስለእኔ ሀሰቶችን ለማሰራጨት ጊዜዋን ሁሉ ታሳልፋለች። አንድ ሺህ ክፍሉን እንኳን ብናገር፣ ብዙ መጻህፍትን ይሞላሉ። ስደቱ ግን በጣም አስቸጋሪ በመሆኑ ማንቸስተርን ትቼ መሄዴ፣ እና ከባለቤቴ ጋር ወደ ፔንስልቬንያ ስቴት በሰስኩሀና ወረዳ መሄዴ አስፈላጊ ሆነ። ለመጀመር እየተዘጋጀን እያለን—በጣም ድሆችም ስለነበርን፣ እና ስደቱም በጣም ከባድ ስለነበረብን ከዚህም የተለየ የምንሆንበት ምንም እድል አልነበረንም—በስቃዮቻችን መካከል ᵐማርቲን ሀሪስ በሚባል

ᵃ፶፯ ሀ ቅ.መ.መ. ስሚዝ፣ ኤማ ሄል።
ᵃ፶፰ ሀ ቅ.መ.መ. ማሳደድ፣ መሳደድ።
ᵃ፶፱ ሀ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡ ፶፪።
ᵃ ለ ቅ.መ.መ. ቅዱሳት መጻህፍት—የሚጠበቁ ቅዱስ መጻፍህት።
ᵃ፰፩ ሀ ት. እና ቃ. ፩፡ ፩።
ᵃ ቅ.መ.መ. ሀሪስ፣ ማርቲን።

የተከበረ ሰው ባልንጀራ አገኘን፣ እርሱም ወደእኛ መጣ እና ለጉዞአችን እንዲረዳን ሀምሳ ዶላሮችን ሰጠን። አቶ ሀሪስ በኒው ዮርክ ስቴት የፓልማይራ ከተማ፣ የዌይን ወረዳ ነዋሪ፣ እና የተከበረ ገበሬም ነበር።

፳፪ በዚህ በጊዜአዊው እርዳታ ወደምሄ ድበት ስፍራ ወደ ፔንስልቬንያ እንድደርስ አስቻለኝ፤ እና እዚያም እንደደረስኩ ወዲ ያውም የሰሌዳውን ፊደሎች መጻፍ ጀመር ኩኝ። ብዙዎችንም ጻፍኩ፣ እና ″ኡሪምና ቱሚምን በመጠቀም አንዳንዶቹን ተረ ጎምኩ፣ ይህንም ያደረኩት በሚስቴ አባት ቤት ከደረስኩበት፣ ከታህሳስ ወር፣ እና በሚቀጥለው የካቲት መካከል ነበር።

፳፫ በዚህ የካቲት ወር ውስጥ አንዴ ከዚህ በፊት የተጠቀሰው አቶ ማርቲን ሀሪስ ወደ ስፍራችን መጣ፣ ከሰሌዳዎቹ የጻፍኳቸ ውን ፊደሎች ወሰደ፣ እና ወደ ኒው ዮርክ ከተማ ይዞአቸው ሄደ። በእርሱ እና በፊደ ሎቹ ስለደረሰባቸው በሚመለከት፣ ሲመ ለስ ለእኔ እንደነገረኝ፣ ስለጉዳዮቹ ታሪክ ወደተናገራቸው አመለክታለሁ፣ ይህም እንዲህ ነበር፥

፳፬ “ወደ ኒው ዮርክ ከተማ ሄጄ የተተ ረጎሙትን ፊደላት፣ እና ትርጉማቸውን በድርሰት ችሎታቸው ታዋቂ ወደ ነበሩት ክብር ሰው ፕሮፌሰር ቻርልስ አንቶን ወሰ ድኩኝ። ፕሮፌሰር አንቶን ትርጉሙ ከዚህ በፊት ከግብጻውያን ትርጉሞች ካያቸው ሁሉ በላይ ትክክል እንደሆነ ነገረኝ። ከዚ ያም ያልተተረጎሙትን አሳየሁት፣ እና እነ ርሱ ግብጻውያን፣ ችሃልዴይክ፣ አሲርኛ፣ እና አረባዊ ናቸው አለ፤ እና እነዚህ እውነ ተኛ ፊደላት ናቸው አለ። ለፓልማይራ ህዝ ቦች እነዚህ እውነተኛ ፊደላት እንደሆኑ፣ እና ትርጉሞቹ እንደተተረጎሙት ትክክል እንደሆኑ የሚያሳይ የምስክር ወረቀትንም ሰጠኝ። የምስክር ወረቀቱን ወሰድኩኝ እና በኪሴ ውስጥ አስቀመጥኩት፣ እና ቤቱን ትቼ ለመሄድ ስወጣ፣ አቶ አንቶን ጠራኝ፣ እና ወጣቱም ሰው እንዴት ባገኛቸው ስፍራ የወርቅ ሰሌዳዎች እንደነበሩ እንዳወቀ ጠየ ቀኝ። የእግዚአብሔር መልአክ ገለጠለት ብዬ መለስኩኝ።

፳፭ “ከዚያም እንዲህ አለኝ፣ ‘የምስ ክር ወረቀቱን ልየው።’ ከኪሴም አውጥቼ ሰጠሁት፣ ሲወስደውም አሁን ″የመላእክት አገልግሎት የሚባል ነገር እንደሌለ፣ እና ሰሌዳዎቹን ወደእርሱ ባመጣቸው እንደሚ ተረጉማቸው በመናገር ቀደደው። የሰሌዳ ዎቹ ክፍሎች የተዘጉ እንደሆኑ፣ እና እኔም እንዳላመጣቸው የተከለከልኩኝ እንደሆነም ነገርኩት። እንዲህም መለሰልኝ፣ ‘″የታሸገ መፅሀፍ ማንበብ አልችልም።’ ከእርሱ ተለ ይቼ ወደ ዶክተር ሚችል ሄድኩኝ፣ እር ሱም ፕሮፌሰር አንቶን ስለፊደላቱ እና ስለትርጉማቸው በሚመለከት የተናገረ ውን ደገፈ።”

. . . . . .

ኦሊቨር ካውደሪ መፅሐፈ ሞርሞንን በሚ ተረጎምበት ጸሀፊ በመሆን አገለገለ—ጆሴፍ እና ኦሊቨር ካውደሪ የአሮናዊ ክህ ነት ከመጥመቁ ዮሐንስ ተቀበሉ—እነር ሱም ተጠመቁ፣ ተሾሙ፣ እናም የትንቢት መንፈስን ተቀበሉ። (አንቀፅ ፳፯–፴፫።)

፳፯ በሚያዝያ ፭ ቀን፣ ፲፰፻፳፭ (እ.አ.አ.) ″ኦሊቨር ካውደሪ ወደቤቴ መጣ፣ እስከዚህ ጊዜ ድረስ አይቼው አላውቅም ነበር። አባቴ በሚኖርበት መንደር ትምህርት ያስተምር እንደነበር፣ እና አባቴ ልጆችን ወደ ትም ህርት ቤት ከሚልኩት አንዱ በመሆኑ፣ በእ ርሱ ቤት ለጊዜው ለመኖር እንደሄደ፣ እዚ ያም እያለ ቤተሰብ ሰሌዳዎችን የተቀበልኩ ባቸውን ጉዳይ እንደነገሩት፣ እና በዚህም መሰረት እኔን ለመጠየቅ እንደመጣ ነገረኝ።

፳፰ አቶ ካውደሪ ከመጣ ሁለት ቀናት

፳፪ ″ ቅ.መ.መ. ኡሪም እና ቱሚም።
፳፭ ″ ቅ.መ.መ. መላእክት።
″ ኢሳ. ፳፱፡፲፩–፲፪፣ ፪ ኔፊ ፳፯፡፲፣ ኤተር ፭፡፩–፯።
፳፯ ″ ቅ.መ.መ. ካውደሪ፣ ኦሊቨር።

ካለፉ በኋላ (ሚያዝያ ፯ ሆኖ)፣ መፅሐፈ ሞርሞንን መተርጎም ቀጠልኩኝ፣ እና እር ሱም ለእኔ መጻፍ ጀመረ።

. . . . . .

፳፯ የትርጉም ስራውን ቀጠልን፣ በሚቀጥለውም ወር [ግንቦት፣ ፲፰፻፳፰ (እ.አ.አ.)]፣ አንድ ቀን ወደ ቁጥቋጣ ዎቹ በመሄድች ለመጸለይ እና በሰሌዳ ዎች ትርጉም ውስጥ ስለተጠቀሱት [a]ለኃ ጢአት ስርየት [b]መጠመቅን በሚመለከት ጌታን ለመጠየቅ ሄድን። እየጸለይን እና ጌታን እየጠራን ሳለን፣ የሰማይ [c]መልእ ክተኛ [d]በብርሀን ዳመና ወረደ፣ እና [e]እጆ ቹን በራሳችን ላይ በመጫን እንዲህ በማ ለት ፦

፳፱ *በእናንተ አገልጋይ ባልንጀሮቼ ላይ፣ የመላእክትን፣ እና የንስሃ ወንጌልን፣ እና ለኃጢአት ስርየት በማጥለቅ የመጠመ ቅን አገልግሎት ቁልፎች የያዘውን የአሮ ንን [f]ክህነት በመሲሁ ስም ለእናንተ እሰ ጣችኋለሁ፤ እናም [g]የሌዊ ልጆች እንደ ገና መስዋዕት ለጌታ በጽድቅ እስከሚሰዉ ድረስ ይህ ከምድር ላይ ዳግመኛ በፍጹም አይወሰድም።*

፴ ይህ የአሮናዊ ክህነት እጆችን በመጫን የመንፈስ ቅዱስ [h]ስጦታን የመስጠት ሀይል እንደሌለው፣ ነገር ግን ይህም ከዚህ በኋላ እንደምንሾምበት ነገረን፣ እና እንድንሄድ እና እንድንጠመቅ አዘዘን፣ እና እኔ ኦሊ ቨር ካውደሪን እንዳጠምቅ፣ እና ከዚያም በኋላ፣ እርሱ እንዲያጠምቀኝ መመሪያዎ ችን ሰጠን።

፴፩ በዚህም መሰረት ሄድን እና ተጠመ ቅን። እርሱን መጀመሪያ አጠመቅሁት፣ እና በኋላም እርሱ እኔን አጠመቀኝ—ከዚ ያም በኋላ እጆቹን በራሱ ላይ በመጫን ለአሮናዊ ክህነት ሾምኩት፣ በኋላም እርሱ እጆቹን ጭኖብኝ ለዚህ አይነት ክህነት ሾመኝ—እኛ እንደዚህም ታዘን ነበርና።*

፴፪ በዚህ ጊዜ የነበኘን እና ይህን ክህ ነት ለእኛ የሰጠን መልእክተኛ ስሙ በአ ዲስ ኪዳን ውስጥ [i]መጥምቁ ዮሐንስ ተብሎ የተጠራው፣ ዮሐንስ እንደነበር፣ እና ይህን ያደረገውም [j]የመልከ ጼዴቅ ክህነት [k]ቁል ፎችን በያዙት [l]በጴጥሮስ፣ [m]ያዕቆብ፣ እና [n]ዮሐንስ አመራር እንደሆነ ነገረን፣ ይህም ክህነት በጊዜው ለእኛ እንደሚሰጠን፣ እና እኔም የቤተክርስቲያኗ የመጀመሪያ [o]ሽማ ግሌ፣ እና እርሱም (ኦሊቨር ካውደሪ) ሁለ

*ኦሊቨር ካውደሪ እነዚህን ሁኔታዎች እንደዚህ ገለጠ፥ “እነዚህ በምንም የማይረሱ ቀናት ነበሩ—በሰማይ መነሳሳት በታገዘ ድምጽ በታች መቀመጥ፣ የዚህን ልብ ታላቅ ምስጋናን ያስነሳል! ከቀን ወደ ቀን፣ ሳይቋረጥ፣ በኡሪምና ቱሚም ወይም ኔፋውያን እንደሚሉትም ‘መተርጓሚያዎችን’ በመጠቀም፣ ‘መፅሐፈ ሞርሞን’ የሚ ባለውን ታሪክ ወይም መዝገብ ከአፉ ለመጻፍ ቀጠልኩኝ።

“በሞርሞን እና በታማኝ ልጁ ሞሮኒ የተሰጡትን የሚያስደንቁ በሰማይ ተወደው እና ተደግፈው የነበሩ ህዝ ቦችን ታሪክ በጥቂት ቃላት መጥቀስ አሁን ካለኝ እቅዴ በላይ ነው፤ ስለዚህ ይህን ለመጨው ጊዜ እተወዋለሁ፤ እና በመግቢያው እንዳልኩት በዚህ ቤተክርስቲያን መነሻ ጊዜ ስለነበሩት፣ በአክራሪዎች መናደድ እና በግ ብዞች አሉባልታ መካከል ወደፊት ለሄዱት እና የክርስቶስን ወንጌል ለተቀበሉት የሚያስደስታቸው አንዳንድ ጥቂት ጉዳዮች ጋር ስለተያያዙት እፅፋለሁ።

“ንጹህ አለመሆን በሰዎች መካከል የሚጠቀሙበት ሁሉም አይነት ድርጅቶች እና ዘዴዎች ላይ አለመረጋ

፳፯ *a* ቅ.መ.መ. የኃጢያት ስርየት።
b ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣ መጥመቅ።
c ቅ.መ.መ. መጥምቁ ዮሐንስ።
d ዘኍሌ. ፲፩፡፳፭፤ ኤተር ፪፡፱–፲፡ ፲፱፤ ት. እና ቃ. ፴፱፡፲።
e ኢ.አ. ፩፡፲።
ቅ.መ.መ. እጅን መጫን።
f ቅ.መ.መ. መሾም፣ ሹመት፤ ስልጣን።
፳፱ *a* ቅ.መ.መ. አሮናዊ ክህነት።
b ዘዳግ. ፣፡፲፤ ት. እና ቃ. ፲፫፣ ፲፰፡፲፱፡፴፱። ቅ.መ.መ. ሌዊ—የሌዊ ጎሳ።
c ቅ.መ.መ. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ።
d ቅ.መ.መ. መጥምቁ ዮሐንስ።
e ቅ.መ.መ. የመልከ ጼዴቅ ክህነት።
f ቅ.መ.መ. ክህነት ቁልፎች።
g ት. እና ቃ. ፴፯፡፲፡–፲፫። ቅ.መ.መ. ጴጥሮስ።
h ቅ.መ.መ. ያዕቆብ፣ የዘብዴዎስ ልጅ።
i ቅ.መ.መ. ዮሐንስ፣ የዘብዴዎስ ልጅ።
j ቅ.መ.መ. ሽማግሌ።

ተኛ ተብለን እንደምንጠራም ነገረን። በዚህ መልእክተኛ እጆች የተሾምንበት እና የተጠመቅንበት ቀን ግንቦት አስራ አምስት፣ ፲፰፻፳፰ (እ.አ.አ.) ነበር።

፳፩ ከተጠመቅን በኋላ ከውሀው ወዲያው ስንወጣ፣ ታላቅ እና የከበሩ በረከቶችን ከሰማይ አባታችን አገኘን። ኦሊቨር ካውደሪን ወዲያው እንዳጠመቅሁት፣ [ሀ]መንፈስ ቅዱስ አረፈበት፣ እና ተነሳ እና በቅርቡ የሚፈጸሙ ብዙ ነገሮችን [ለ]ተነበየ። ደግሞም፣ ወዲያው እኔ እንደተጠመቅሁ፣ ተነስቼ ስለዚህ ቤተክርስቲያን መነሳት፣ እና ቤተክርስቲያኗን እና የዚህ ትውልድ የሰውልጆችን በሚመለከት በብዙ ሌሎች ነገሮች ስተነብይም፣ የትንቢት መንፈስ እኔ ደግሞ ነበረኝ። በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተን ነበር፣ እና በደህንነታችን አምላክ ተደሰትን።

፳፪ አዕምሮአችን አሁን ተብራርተው ቅዱስ መጻህፍት [ሐ]ይገቡን ዘንድ ተከፈቱልን፣ እና የእነዚህ ብዙ ሚስጥራዊ ምን ባቦች [መ]እውነተኛ ትርጉምና እቅድ ከዚህ በፊት ልናገኛቸው በማንችለው፣ ወይም ከዚህ በፊት አስበንባቸው በማንውቀው መንገድ ተገለጡልን። በሰፈራችን ራሱን እያሳየ በነበረው የስደት መንፈስ ምክንያት፣ በዚህም ጊዜ ክህነትን የመቀበላችንን እና የመጠመቃችንን ጉዳይ በሚስጥር ለመጠበቅ ተገድደን ነበር።

፳፫ ከጊዜ ወደ ጊዜም፣ በአመጽ የተነሳሱ ሰዎች አስፈራርተውናል፣ እና ይህም በሀይማኖት በሚያምኑት ነበር። የሚያስፈራሩን አመጸኞች ፍላጎትም የተቆጣጠረው ለእኔ ባልንጀራ እየሆኑ በመጡት፣ እና አመጸኛዎችን በሚቃወሙት፣ እና ያለማቋረጥ የትርጉም ስራን ለመቀጠል እንዲፈቀድልኝ ፍላጎት በነበራቸው በባለቤቴ አባት ቤተሰብ ተፅዕኖ (በመለኮታዊ ጥበቃ) ብቻ ነበር፤ ስለዚህም ህጋዊ ካልሆኑ እርምጃዎች፣ እስከችሎታቸው ድረስ፣ እኛን ለመጠበቅ ፈቃደኛነታቸውን ገለጹ እና ቃል ኪዳንም ገቡልን።

ገጥ በሚያስፋፋበት ጊዜ፣ ማንም ሰው በረጋ ስሜታቸው፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሳኤ የበጎ ህሊናን ለመመለስ የልብ ፈቃድን በማሳየት በውሀ መቃብር ውስጥ የመቀበር መብትን ፍላጎት ያለማሳየት ለኔፋውያን ከአዳኝ አፍ ቤተክርስቲያኑን ሰዎች የሚገነቡበትን ትክክለኛ መንገድ የተሰጣቸውን መመሪያዎች ለመተርጎም እና ለመጻፍ ማናቸውም ሰዎች አይችሉም።

“በዚህ ክፍለ አህጉር ላይ ለያዕቆብ ዘር ቅሪቶች ስለአዳኝ አገልግሎት የተሰጠውን ታሪክ ከተጻፈ በኋላ፣ ነቢዩ ይሆናል እንዳለው ጭለማ ምድርን እና ያልታረመ ጭለማ የህዝቦችን አዕምሮዎች እንደሸፈነ ለማየት ቀላል ነበር። በተጨማሪ በማሰብም ሀይማኖትን በሚመለከት በነበረው ታላቅ ሁካታ እና ጩኸት መካከል፣ የወንጌልን ስነስርዓቶች ለማከናወን ማንም ከእግዚአብሔር ስልጣን እንደሌለው ለማየት ቀላል ነበር። ይህንንም ጥያቄ ሊጠየቅም ይቻላል፣ ምስክሩ ከትንቢት መንፈስ ያነሰ ሳይሆን፣ እና ሀይማኖቱ በሰዎች በምድር በነበረበት በአለም እድሜዎች ሁሉ በራዕይ ላይ በተመሰረቱ፣ በተገነቡ፣ እና በተደገፉ በክርስቶስ ስም፣ ራዕይን የሚክዱ ሰዎች ለማስተዳደር ስልጣን አላቸውን? እነዚህ ነገሮች በሰዎች ፊት ከተገለጹ ስራዎቻቸው አደጋ ላይ በሚሆኑባቸው የተቀበሩትና በጥንቃቄ የተደበቁት እነዚህ እውነቶች ለእኛ ከዚህ በኋላ አልተደበቁም፤ እና ‘ተነሳና ተጠመቅ’ የሚለውን ትእዛዝ እንዲሰጠን ብቻ እንጠብቃለን።

“ይህም እውነት ከመሆኑ በፊት ለብዙ ጊዜ በፍላጎት አልጠበቅንም። በምህረቱ ባለጠጋ የሆነው፣ እና የትሁቱን ዘላቂ ጸሎት ለመመለስ ፍላጎት ያለው ጌታ፣ ሰዎች ከሚኖሩበት ተለይተን፣ ልብ በሚነካ አኳኋን ከጠራነው በኋላ፣ ፈቃዱን ለእኛ ለማሳየት ወረደ። በድንገት፣ ከዘለአለም መካከል እንደሆነ አይነት፣ መጋረጃው ተከፈተ እና የእግዚአብሔር መልአክ በክብር ልብስ ተሸፍኖ፣ እና በጉጉት ይጠበቅ የነበረውን መልእክት፣ እና የንስሀን ወንጌል ቁልፎችን ለመስጠት ሲወርድ፣ የአዳኝ ድምፅ ሰላምን ተናገረን። ምን አይነት ደስታ! ምን አይነት ድንቅ! እንዴት ያስገርማል! አለም በጣም እየተቸገረ እና እየተምታታ እያለ—ሚልዮኖችም እንደ አይነ ስውር ግድግዳን ለመንካት በዳበሳ ሲፈልጉ፣ እና ሁሉም ሰዎች በማይረጋገጥ ነገር ላይ እየተመኩ እያሉ፣ እንደ ‘ቀትር ብርሀን’ አይነት አይኖቻችን አዩ፣ ጆሮዎቻችንም ሰሙ፤ አዎ፣ ተጨማሪም—በፍጥረት ፊት ላይ ብሩህነቱን እንደሚጥለው ከግንቦት የጸሀይ ብርሀን መንጸባረቅ በላይ! ከዚያም ድምጹ፣ ረጋ ያለ ቢሆንም፣ ውስጥን ሰንጥቆ

[ሀ] ሀ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።

[ለ] ለ ቅ.መ.መ. ትንቢት፣ መተንበይ።

[ሐ] ሐ ቅ.መ.መ. ማስተዋል።

[መ] መ ዮሐ. ፲፮፣ ፲፫።

የሚገባ ነበር፣ እና ‘እኔ ከእናንተ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ’ ያለው ቃላቶቹ እያንዳንዱን ፍርሀት በተናቸው። አዳ መጥን፣ አተኮርን፣ ተገረምን! ይህም ከክብር የመጣ የመልአክ ድምፅ ነበር፣ ይህም ከልዑል የመጣ መልአክ ነበር! ፍቅሩም በነፍሶቻችን ላይ እየተቀጣጠለ እያለ፣ ስናደምጥም ተደሰትን፣ እና ሁሉን በሚገዛ ራዕይ ተጠ ቅልለን ነበር! ለመጠራጠር ምን ስፍራ ነበረ? የትም አልነበረም፤ እርግጠኛ አለመሆን ሸሸ፣ ልብ ወለድ እና ሐሰት ለዘለአለም ሲሸሸም፣ መጠራጠርም እንደገና ላለመነሳት ሰመጠ!

“ነገር ግን፣ ውድ ወንድም፣ አስብ፣ በተጨማሪም ለጥቂት ጊዜ አስብ፣ ልባችንን ምን አይነት ደስታ ሞላው፣ እና በምን አይነት ድንቅ ሰገድን፣ (ለዚህ አይነት በረከት የማን ጉልበቶች ታጥፈው አይሰግዱም?) ከእጆቹ ቅዱስ ክህነትን ስንቀበል እንዲህ አለ፣ ‘አገልጋይ ባልንጀሮቼ፣ የሌዊ ልጆች እንደገና መሰዋዕትን ለጌታ በጽ ድቅ እስኪያቀርቡ ድረስ ይህ ከምድር ላይ ዳግመኛ በፍጹም የማይወሰደውን ይህን ክህነት እና ሀላፊነት በመ ሲሁ ስም ለእናንተ እሰጣችዋኋለሁ!’

“የዚህን ልብ ስሜት፣ ወይም በዚህ ጊዜ የከበበንን ውበት እና ክብር ልገልፅላችሁ አልሞክርም፤ ነገር ግን ምድር ወይም ሰው በጊዜ ልሳን ቅንነት እንደዚህ ቅዱስ ሰው አይነት የሚያስደንቅ ወይም ልብ የሚማርክ ቋንቋ ለማልበስ ለመጀመር አይቻልም ስላችሁ ታምኑኛላችሁ። አይደለም፤ ይህች ምድርም ደስታን የመስጠት፣ ሰላም የመስጠት፣ ወይም በመንፈስ ቅዱስ ሀይል እያንዳንዱ አረፍተ-ነገር ሲሰጡ በውስጣቸው የነበራቸውን ጥበብ ለመረዳት ሀይል የላትም! ሰው ጓደኛውን ለማታለል ይችላል፣ ማታለልም ማታለልን ይከተላል፣ እና የክፉው ልጆችም ሞኞችንና ያልተማሩትን ከልብ ወለድ በስተቀር ምንም ብዙዎችን ለመመገብ እስከማይችል ድረስ ለማዳራት፣ እና የሀሰተኛነት ፍሬም ወረተኛውን ወደመቃብሩ በፍሰቱ ይዞት የሚሄድበት ሀይል ይኖራ ቸው ይችላሉ፣ ነገር ግን በፍቅሩ አንድ ጣት መነካት፣ አዎ፣ ከከፍተኛው አለም አንድ የክብር ጨረር፣ ወይም አንድ ቃል፣ ከዘለአለም እቅፍ፣ ከአዳኝ አንደበት፣ ሁሉንም ዋጋ የሌላቸው ያደርጋቸዋል፣ እና ከአዕምሮም ለዘለአለም ይሰርዛቸዋል። በመልአክ ፊት እንደነበርን ማረጋገጫ፣ የኢየሱስን ድምፅ እንደሰማን ማረጋገጫ፣ እና እውነቱ ሳይበላሽ ከንጹህ ሰውየው በእግዚአብሔር ፈቃድ የቃል ፅህፈት ሳይቋረጥ መምጣቱ ለእኔ መግ ለጫ የማይቻልበት ነው፣ እና በህይወትም እያለሁ በዚህ የአዳኝ መልካምነት መግለጫ ላይም በድንቅ እና በም ስጋና ነው የምመለከተው፤ እና ፍጹምነት በሚኖርበት እና ኃጢአት በምንም በማይገባበት ቤቶች ውስጥ፣ እር ሱን ማለቂያ በሌለው ቀን ውስጥ ላፈቅረው ተስፋ አለኝ።”—*Messenger and Advocate*፣ ቅፅ ፩ [ጥቅምት ፲፰፻፹፬ (እ.አ.አ.)]፣ ገፅ ፲፬–፲፭።

የእምነት አንቀጾች

የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን

በዘለአለማዊ አባት ᵐእግዚአብሔር፣ ᵃበልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ እናም ᵇበመንፈስ ቅዱስ ᶜእናምናለን።

፪ ᵈበአዳም መተላለፍ ሳይሆን፣ ሰዎች ᵃበራሳቸው ኃጢአት እንደሚቀጡ እና ምናለን።

፫ ᵉየወንጌሉን ᵃህግጋትና ስርዓቶችን ᵇበማክበር፣ የሰው ዘር ሁሉ በክርስቶስ ᶜየኃጢአት ክፍያ አማካይነት ᵈመዳን እን ደሚችሉ እናምናለን።

፬ የወንጌሉ ቀዳሚ መሰረታዊ መርሆችና ᵉስርዓቶች፥ አንደኛ፣ በጌታ ኢየሱስ ክርስ ቶስ ᵃእምነት፤ ሁለተኛ፣ ᵇንስሐ መግባት፤ ሶስተኛ፣ ለኃጢአት ᶜስርየት በመጥለቅ ᵈመጠመቅ፤ አራተኛ፣ የመንፈስ ቅዱስን ᵉስጦታ ለመስጠት ᵃእጆችን መጫን እን ደሆኑ እናምናለን።

፭ ሰው ወንጌሉን ᵉለመስበክና በወንጌሉ ᵃስርዓትም ለማገልገል ᵇበትንቢትና ᶜስል ጣን ባላቸው ሰዎች ᵈእጆችን በመጫን በእ ግዚአብሔር ᵉመጠራት እንዳለበት እናም ናለን።

፮ በጥንቷ ቤተክርስቲያን እንደነበረው አንድ አይነት ᵉድርጅት፣ በስምም ᵃበሐዋ ርያት፣ ᵇበነቢያት፣ ᶜበአገልጋዮች፣ በአስ ተማሪዎች፣ ᵈበወንጌል ሰባኪዎችና፣ በሌ ሎችም፣ እናምናለን።

፯ ᵉበልሳን ᵃስጦታ፣ ᵇበትንቢት፣ ᶜበራ ዕይ፣ ᵈበመገለጥ፣ ᵉበመፈወስ፣ ልሳንን ᶠበመተርጎም፣ እናም፤ በመሳሰሉት ስጦ ታዎችም እናምናለን።

፰ ᵉበትክክል እስከተተረጎመ ድረስ፣ ᵃመፅሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ᵇቃል እንደሆነ እናምናለን፤ ደግሞም ᶜመፅሐፈ ሞርሞንም የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ እናምናለን።

፩ ፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ— እግዚአብሔር አብ።
ለ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ፤ እግዚአብሔር፣ አምላክ— እግዚአብሔር ወልድ።
ሐ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ፤ እግዚአብሔር፣ አምላክ—እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ።
መ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
፪ *ሀ* ቅ.መ.መ. የአዳም እና የሔዋን ውድቀት።
ለ ዘዳግ. ፳፬፡፲፮፤ ሕዝ. ፲፰፡፲፱–፳።
ቅ.መ.መ. መልስ መስጠት፣ ሂሳብ፣ ተጠያቂነት፣ ሀላፊነት፤ ነጻ ምርጫ።
፫ *ሀ* ቅ.መ.መ. ወንጌል።
ለ ቅ.መ.መ. ህግ።
ሐ ቅ.መ.መ. ታዛዥነት፣ ታዛዥ፣ መታዘዝ።
መ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ።
ሠ ሞዛያ ፳፯፡፳፩–፳፯፤ ሙሴ ፮፡፱።
ቅ.መ.መ. ደህንነት።
፬ *ሀ* ቅ.መ.መ. ስነስርዓቶች።
ለ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
ሐ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣ ንስሀ መግባት።
መ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ስርየት።
ሠ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣ መጥመቅ።
ረ ቅ.መ.መ. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ።
ሰ ቅ.መ.መ. እጅን መጫን።
፭ *ሀ* ቅ.መ.መ. መስበክ።
ለ አልማ ፲፫፡፳–፲፯።
ሐ ቅ.መ.መ. ትንቢት፣ መተንበይ።
መ ቅ.መ.መ. ስልጣን፤ ክህነት።
ሠ ቅ.መ.መ. እጅን መጫን።
ረ ቅ.መ.መ. ጥሪ፣ በእግዚአብሔር መጠራት፣ የተጠራበት።
፮ *ሀ* ቅ.መ.መ. የእውነተኛ ቤተክርስቲያን ምልክቶች— የቤተክርስቲያን ድርጅት።
ለ ቅ.መ.መ. ሐዋሪያ።
ሐ ቅ.መ.መ. ነቢይ።
መ ቅ.መ.መ. ኤጲስ ቆጶስ።
ሠ ቅ.መ.መ. ወንጌል ሰባኪ፤ የአባቶች አለቃ፣ ፓትሪያርክ።
፯ *ሀ* ቅ.መ.መ. የልሳኖች ስጦታ።
ለ ቅ.መ.መ. የመንፈስ ስጦታዎች።
ሐ ቅ.መ.መ. ትንቢት፣ መተንበይ።
መ ቅ.መ.መ. ራዕይ።
ሠ ቅ.መ.መ. ራዕይ።
ረ ቅ.መ.መ. መፈወስ፣ ፈውሶች።
ሰ ፩ ቆሮ. ፲፪፡፲፤ ሞር. ፱፡፯–፳።
፰ *ሀ* ፩ ኔፊ ፲፫፡፳–፳፣ ፲፱፡፳–፳፯።
ለ ቅ.መ.መ. መፅሐፍ ቅዱስ።
ሐ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ቃል።
መ ቅ.መ.መ. መፅሐፈ ሞርሞን።

፱ እግዚአብሔር እስካሁን ᵐበገለጣቸው ሁሉ፣ አሁንም በሚገልጣቸው ሁሉ እና ምናለን፣ እናም የእግዚአብሔርን መንግስት በተመለከተ ወደፊትም እርሱ ᵃበሚገልጣቸው ታላቅና አስፈላጊ ነገሮችም እና ምናለን።

፲ ስለእስራኤል ᵐመሰብሰብና ስለ ᵃአስሩ ነገዶች ዳግሞ መመለስ፣ ᵇፅዮንም (አዲሲቷ ኢየሩሳሌም) በአሜሪካ ክፍለ አህጉር እንደምትገነባ፣ ክርስቶስ እራሱም በምድር ላይ ᶜእንደሚነግስ፣ እናም ምድርም ᶜታድሳ ᶜገነታዊ ᵃክብሯን እንደምትቀበልም እናምናለን።

፲፩ ሁሉን የሚገዛው እግዚአብሔርን ᵐህሊናችን ᵃእንደሚመራን የማምለክ ᵇመብት እንዳለን እናረጋግጣለን፣ እናም ሁሉም ሰዎች እንዴትም፣ የትም፣ ወይም ምንም የፈለጉትን ምንም ᶜእንዲያመልኩ እንደዚህ አይነት መብት እንዳላቸውም እንቀበላለን።

፲፪ ለንጉሶች፣ ለፕሬዘደንቶች፣ ለገዢዎች፣ እናም ለዳኞች ታዛዦች በመሆን፣ ᵐህግን በመታዘዝ፣ በማክበርና በመደገፍ እናምናለን።

፲፫ ᵐበታማኝነት፣ በእውነተኛነት፣ ᵃበንፅህና፣ በቸርነት፣ በምግባረ መልካምነት፣ እናም ለሁሉም ሰዎች ᵇበጎ ነገሮችን አድራጊ በመሆን እናምናለን፤ በርግጥም የጳውሎስን ᶜምክርም እንከተላለን ለማለት እንችላለን—በሁሉም ነገሮች እናምናለን፣ በሁሉም ነገሮች ᶜተስፋ እናደርጋለን፣ በብዙ ነገሮች ፀንተናል፣ እና በሁሉም ነገሮች ᵈመፅናት ስለመቻል ተስፋ አለን። ᵃምግባረ መልካም፣ የሚያስደስት፣ ወይም መልካም ሀተታ ወይም ምስጋና የሚገባው ምንም ነገር ቢኖር፣ እኛም እነዚህን እንሻለን።

ጆሴፍ ስሚዝ።

፱ *ሀ* ቅ.መ.መ. ራዕይ።
ለ ዓሞ. ፫፡፲፣ ትእ. ኤፍ. ፲፫፡፲–፲፮። ቅ.መ.መ. ቅዱሳት መጻህፍት—እንደሚመጡ የተተነበዩ ቅዱሳት መጻህፍት።

፲ *ሀ* ኢሳ. ፴፱፡፳–፳፪፣ ፳፡፩፣ ፩ ኔፊ ፲፱፡፣ ፲፭–፲፯። ቅ.መ.መ. እስራኤል—የእስራኤል መሰብሰብ።
ለ ቅ.መ.መ. እስራኤል—የጠፉት የእስራኤል አስር ጎሳዎች።
ሐ ኤተር ፲፫፡፪–፲፩፣ ትእ. ኤፍ. ፴፭፡፳፯–፳፯፣ ፴፡፲፪፡፪–፭፣ ሙሴ ፯፡፲፣ ፲፳። ቅ.መ.መ. አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፣ ፅዮን።
መ ቅ.መ.መ. አንድ ሺህ አመት።
ሠ ቅ.መ.መ. ምድር—ምድርን ማፅዳት።
ረ ይህም በዓደን ገነት እንደነበረው ሁኔታ የማለት ነው፣ ኢሳ. ፲፩፡፮–፱፣ ፴፭፣ ፶፭፡፩–፫፣ ፳፭፡፳–፳፭፣ ፲፯–፳፭፣ ሕዝ. ፴፯፡፴፭። ቅ.መ.መ. ገነት።
ሰ ቅ.መ.መ. ክብር።

፲፩ *ሀ* ቅ.መ.መ. ህሊና።
ለ ቅ.መ.መ. ነጻ ምርጫ።
ሐ ት. እና ቃ. ፲፴፬፡፩–፲፩።
መ ቅ.መ.መ. ማምለክ።

፲፪ *ሀ* ት. እና ቃ. ፶፡፳፡፳፭–፳፫። ቅ.መ.መ. ህግ።

፲፫ *ሀ* ቅ.መ.መ. ቅንነት፣ ታማኝ፣ ታማኝነት።
ለ ቅ.መ.መ. ንጹህነት።
ሐ ቅ.መ.መ. አገልግሎት።
መ ፊልጵ. ፬፡፰።
ሠ ቅ.መ.መ. ተስፋ።
ረ ቅ.መ.መ. መፅናት።
ሰ ቅ.መ.መ. መጠነኛነት፣ በንነት።

ተጨማሪ መግለጫ

የቅዱሳት መጻህፍት መመሪያ

የዘመን ቅድመ ተከተል

የወንጌሎች ስምምነት

የጆሴፍ ስሚዝ ትርጉም

የመፅሐፍ ቅዱስ ካርታዎች

የመፅሐፍ ቅዱስ ፎቶዎች

የቤተክርስቲያኗ ታሪክ ካርታዎች

የቤተክርስቲያኗ ታሪክ ፎቶዎች

የቅዱሳት መጻህፍት መመሪያ

የቅዱሳት መጻህፍት መመሪያ በመፅሐፍ ቅዱስ፣ በመፅሐፈ ሞርሞን፣ በትምህርት እና ቃል ኪዳኖች፣ እና በታላቅ ዋጋ ዕንቁ ውስጥ የሚገኙትን የተመረጡ ትምህርቶችን፣ መስረታዊ መመሪያዎችን፣ ሰዎች፣ እና ቦታዎችን የሚያብራራ ነው። ይህም ለእያንዳንዱ ርዕስ ጥናታችሁ ዋና የቅዱሳት መጻህፍት ማጣቀሻ ያቀርብ ላችኋል። ይህ መመሪያ በግል እና በቤተሰባችሁ የቅዱሳት መጻህፍት ጥናት ሊረዳችሁ ይችላል። ስለወንጌል ያላችሁን ጥያቄ ለመመለስ፣ ለቅዱሳት መጻህፍት ርዕሶች ጥናት፣ ንግግሮች እና ትምህርቶችን ለማዘጋጀት፣ እና ስለወንጌል ያላችሁን እውቀት እና ምስክር ለማሳደግ ይረዳችኋል።

የሚቀጥለው ስዕላዊ መግለጫ በቅዱሳት መጻህፍት መመሪያ ውስጥ የሚገኘው ጥቅስት ምሳሌን ይገልጻል።

ርዕሶች የሚጻፉት በደማቅ ጽሁፍ ፊደሎች ናቸው።

ምድር። ደግሞም መፍጠር፣ ፍጥረት፤ አለም

ተመልከቱ

አንዳንዴም በመመሪያው ውስጥ የሚገኙት ሌሎች ርዕሶች ከምታጠኑት ርዕስ ጋር የሚገናኙ መረጃ ዎችን የያዙ ይሆናሉ። ደግሞም. . .*ተመልከቱ* የሚሉት ቃላት ወደ ተገናኙት ርዕሶች ይመሯችኋል።

ርዕሶቹም በተጨማሪ አጭር ትርጉም አላቸው።

በእግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ሰው በስ ጋዊ ሙከራ ጊዜው እንዲጠቀሙበት የተፈጠረ የምን ኖርበት ፕላኔት። የመጨረሻ እጣ ፈንታዋ የምትከበ ርና ከፍ የተደረገች መሆን ነው (ት. እና ቃ. ፹፯፤ ፩–፪፤ ፻፴፤ ፷–፱)። ምድር ለሰለስቲያል ክብር ብቁ ሆነው ለኖሩት ዘለአለማዊ ውርስ ትሆናለች(ት. እና ቃ. ፹፰፤ ፲፡–፳፯)። እነርሱም በአብና ወልድ ፊት በመ ኖር ይደሰታሉ (ት. እና ቃ. ፳፯፤ ፷፤ ፹)።

ትርጉሙ እንዲገባችሁ የሚያ ደርጉ የቅዱሳት መጻህፍት ጥቅሶችም በ ቅንፎች ውስጥ ይገኛሉ።

አንዳንዶቹ ርዕሶች አነስተኛ ርዕሶች አሏቸው። እነዚህም ጠመም ባለ የፊደል አጣጣል የተጻፉ ናቸው።

ለሰው የተፈጠረች ነች: እግዚአብሔር በምድር ላይ ገዝ አደረጋቸው, **ዘፍጥ.** ፩፤ ፳፰ (ሙሴ ፪፤ ፳፰). ምድሪቱ የእግዚአብሔር ነች, **ዘፀአ.** ፱፤ ፳፪ (መዝ. ፳፬፡፩). ምድርን ጌታ ለሰው ልጆች ሰጣት, **መዝ.** ፻፲፭፤ ፲፮. እኔ ምድርን ሠርቻለሁ ሰውንም በእርስዋ ላይ ፈጥሬአለሁ, **ኢሳ.** ፵፭፤ ፲፪.

ሰው በቃሉ ኃይል ወደ ምድር ፊት መጥቷል, **ያዕቆ.** ፬፤ ፱.

እያንዳንዱ የቅዱስ መፅሐፍ ጥቅስ በቅዱስ መፅሀፉ አጭር ጥቅስ ወይም የቅዱስ መፅሐፍ ማጠቃለያ አላቸው።

ምድር መንፈስ ቅዱስን እንደ መሪያቸው ለወሰ ዱት ትሰጣለች, **ት. እና ቃ.** ፵፭፤ ፻፲፮–፻፴፯ (ት. እና ቃ. ፻፲፡፤ ፯). ወንጌሌን ያከበሩ የምድር ጥሩ ነገሮች የእነ ርሱ ደመወዛቸው ይሆናል, **ት. እና ቃ.** ፻፱፤ ፲. ድሀ ውና የዋሁ ምድርን ይወርሳሉ, **ት. እና ቃ.** ፹፯፤ ፲፯ (ማቴ. ፭፤ ፭; ፲ ኔፊ ፲፪፤ ፭).

ከእዚያ ርዕሶች ጋር የተያያዙ ቅዱሳት መጻህፍት ጥቅሶች በቅንፎች ውስጥ ይገኛሉ።

ምድርን እንሰራለን፣ እናም እንፈትናቸዋለን, **አብር.** ፲፤ ፳፬–፳፭.

ከሞት መነሳት። ትንሳኤ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ

ተመልከቱ

አንዳንዴም የርዕሱ መረጃ ከተመለከታችሁት ርዕስ በታች አይገኝም። *ተመልከቱ* የሚለው ቃል መረጃው ወደ ሚገኝበት ርዕስ ይመራ ችኋል።

የምድር ዳርቻ። አለም—የአለም መጨረሻ

ተመልከቱ

መስመር የሚከተለው *ተመልከቱ* (ወይም *ደግሞም. . .ተመልከቱ*) የሚለው ቃል መረጃው ታናሽ መግቢያ ("የአለም መጨረሻ") በዋና ርዕሱ ("አለም") ውስጥ እንደሚገኝ ይነግሯችኋል።

ሀላፊነት፣ ሀላፊ። *ደግምም መሾም፣ ሹመት፤ ክህነት ተመልከቱ*

በድርጅት ውስጥ ያለ ስልጣን፣ ብዙ ጊዜ በቅዱሳት መጻህፍት ውስጥ የክህነት ሀላፊነትን ለመ ጠቆም የሚጠቀሙበት ነው፤ ይህም ለስራ ደረጃው የተመደበ ሀላፊነትን ወይም የስራ ደረጃን የሚይዘ ውን ሰው የሚጠቁም ሊሆንም ይችላል።

የአባላት ሁሉ ሥራ አንድ እንዳይደለ፣ **ሮሜ ፲፪፡፩**።

ኃላፊነታችንን ለጌታ አጎላን፣ **ያዕቆ. ፩፡፲፱**። መልከ ፄዴቅ የሊቀ ካህንነት ሀላፊነትን ተቀበለ፣ **አልማ ፲፫፡፲፰**። የመላእክት አገልግሎት ኃላፊነ ታቸው ሰዎችን ወደ ንሰሃ መጥራት ነው፣ **ሞሮኒ ፯፡፴፩**።

ካለቤተክርስቲያኗ ምርጫ ማንም ሰው በቤ ተክርስቲያን ሀላፊነት አይሾምም፣ **ት. እና ቃ. ፳፡፡፡፳**። እያንዳንዱ ሰው በተሾመበት ይቁም፣ **ት. እና ቃ. ፸፬፡፲፬**። ፕሬዘደንቶች፣ ወይም ከተ ለያዩ ከእነዚህ የክህነት ስልጣኖች ውስጥ በተላያዩ ሀላፊነቶች ከተሾሙት መካከል የሚመጡ ወይም የሚሾሙ መሪዎች አሉ፣ **ት. እና ቃ. ፲፯፡፳፭**። የክህነት ቡድኖችን የሚመሩት ሀላፊነቶች ተገ ልጸዋል፣ **ት. እና ቃ. ፲፯፡፸፫–፸፡፡**። እያንዳ ንዱም ወንድ ሰው ሀላፊነቱን እና በተመደበበት ሀላፊነት በቅንነት መስራትን ይማር፣ **ት. እና ቃ. ፲፯፡፶፱–፷**። ለእናንተ ለክህነት ስልጣኔ አባል የሆ ኑትን ባለስልጣኖች እሰጣችኋለሁ፣ **ት. እና ቃ. ፲፳፡፲፡፲፳**።

ሀሜት። *አሉባልታ ተመልከቱ*

ሀሪስ፣ ማርቲን። *ደግምም የመፅሐፈ ሞርሞን ምስክሮች ተመልከቱ*

ስለመፅሐፈ ሞርሞን መለኮታዊ ስነ ነገርነት እና እውነተኛነት ምስክር ከሆኑት ከሶስት አንዱ። ለጆሴፍ ስሚዝን እና ለቤተክርስቲያኗን በገንዘብ እርዳታ ሰጠ። ጌታ ማርቲን ሀርስን ንብረቱን እን ዲሸጥ እና ገንዘቡን መፅሐፈ ሞርሞንን ለማተም እንዲሰጥ (ት. እና ቃ. ፲፱፡፳፯–፳፯፣ ፴፪–፴፭)፣ ለቤተክርስቲያኗ ምሳሌ እንዲሆን (ት. እና ቃ. ፶፡፡፡፴)፣ እና የአገልግሎትን ወጪ እንዲከፍል ጠየቀው (ት. እና ቃ. ፲፱፡፳፯)።

ማርቲን ሀርስ ከቤተክርስቲያኗ ተወገዘ ነገር ግን በኋላም ወደ ሙሉ አባልነት ተመለሰ። እስከ ህይ ወቱ መጨረሻ ድረስ መልአኩ ሞሮኒን እና ጆሴፍ ስሚዝ መፅሐፈ ሞርሞንን የተረጎመበትን የወርቅ ሰሌዳዎችን እንዳየ መሰክሯል።

ሀሳብን የመረዳት ስጦታ። *የመለየት ስጦታ ተመልከቱ*

ሀሳቦች። *ደግምም ማሰላሰል፤ ነጻ ምርጫ ተመልከቱ*

በሰው አዕምሮ ውስጥ የሚገኝ አስተያየት፣ ግን ዛቤ፣ እና ቅርፅ የማሰብ ሀይል የእግዚአብሔር ስጦታ ነው፣ እናም የማሰብ ሀይላችንን እንዴት እንደም ንጠቀምባቸው ለመምረጥ ነጻ ነን። አስተሳሰባችን አስተያየታችን እና ጸባያችን ላይ፣ እንዲሁም ከዚህ ህይወት በኋላ በሚኖረን ህይወት ላይ ተፅዕኖ አለው። ጻድቅ ሀሳቦች ወደ ደህንነት ይመራሉ፣ ክፉ ሀሳቦች ወደ መከነን ይመራሉ።

እግዚአብሔር የነፍስንም አሳብ ሁሉ ያውቃል፣ **፩ ዜና ፳፰፡፱**። በልቡ እንዳሰበ እንዲሁ ነው፣ **ምሳ. ፳፫፡፯**። አሳቤ እንደ አሳባችሁ አይደሉም፣ **ኢሳ. ፶፭፡፯–፱**።

ኢየሱስ ግን አሳባቸውን አወቀ፣ **ማቴ. ፲፪፡፳፭** (ሉቃ. ፭፡፳፪፣ ፮፡፡)። ከውስጥ ከሰው ልብ የሚ ወጣ ክፉ አሳብ ይመጣል፣ **ማር. ፯፡፳–፳፫**። ለክ ርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን፣ **፪ ቆሮ. ፣፡፭**። መልካም ወሬ ያለበትን ነገር ሁሉ፡ በጎነት ቢሆን ምስጋናም ቢሆን፡ እነዚህን አስቡ፣ **ፊልጵ. ፬፡፰**።

ስለዓለም ማሰብ ሞት እንደሆነና፣ ስለመንፈ ሳዊ ነገር ማሰብ ዘለዓለማዊ ህይወት እንደሆነ አስ ታውሱ፣ **፪ ኔፊ ፱፡፴፱**። ራሳችሁን፣ እናም ሀሳባ ችሁን፣ የማታስተውሉ ከሆናችሁ፣ መጥፋት ይገ ባችኋል፣ **ሞዛያ ፬፡፴**። ሀሳባችንም ደግሞ ይፈር ድብናል፣ **አልማ ፲፪፡፲፬**።

ከእግዚአብሔር ብቻ የሃሳብህንና የልብህን ፈቃድ ያውቃል፣ **ት. እና ቃ. ፮፡፲፮** (ት. እና ቃ. ፴፣፡፩)። በማንኛውም ሃሳብ ወደእኔ ተመልከቱ፣ **ት. እና ቃ. ፮፡፴፮**። የህይወትን ቃል በአዕምሮዎቻችሁ ውስጥ አከማቹ፣ **ት. እና ቃ. ፹፬፡፹፭**። ጥቅም የሌላቸ ውን ሀሳቦቻችሁን ጣሉ፣ **ት. እና ቃ. ፹፯፡፴፱**። የሰዎችን የልባቸውን ሀሳቦቻቸውን ይገልጻል፣ **ት. እና ቃ. ፹፯፡፲፱**። ምግባረ ጥሩነትም ሀሳብ ህን ያሳምር፣ **ት. እና ቃ. ፲፳፭፣ ፶፭**።

የእያንዳንድ ሰው አሳብ ሁልጊዜ ፈጽሞ ክፉ ሆነ፣ **ሙሴ ፰፡፳፭**።

ሀብቶች። *ደግምም ኩራት፤ ገንዘብ ተመልከቱ*

መትረፍረፍ ወይም ሀብት። ጌታ ቅዱሳንን በእ ነዚያ ጥሩ ለማድረግ ካልሆነ በቀር አለማዊ ሀብቶ ችን እንዳይፈልጉ መክሯል። ቅዱሳን የአለም ሀብ ትን ከመፈለጋቸው በፊት፣ የዘለአለም ሀብቶች የያ ዘውን የእግዚአብሔር መንግስት መፈልግ ይገባቸ ዋል፣ (ያዕቆ. ፪፡፲፰–፲፱)።

ባለጠግነት ቢበዛ ልባችሁ አይኩራ፣ **መዝ. ፷፪፡፲**። በቀጣ ቀን ሀብት አትረባም፣ **ምሳ. ፲፩፡፬**። በባለጠግነቱ የሚተማመን ሰው ይወድቃል፣ **ምሳ.**

፲፭፡፳፯። መልካም ስም ከብዙ ባለጠግነት ይሻላል፣ ምሳ. ፳፪፡፩።

ገንዘብ ላላቸው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት እንዴት ጭንቅ ይሆናል፣ ማር. ፲፡፳፫ (ሉቃ. ፲፰፡፳፭–፳፮)። ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነው፣ ፩ ጢሞ. ፮፡፲።

ሀብታም በመሆናቸው ድሆችን ለሚጠሉት ወዮ ላቸው፣ ፪ ኄሬ ፪፡፴። ጻድቃን ልባቸውን በሀብቶች ላይ አላስቀመጡም ነገር ግን ከሁሉም ጋር ተካፈሉ፣ አልማ ፩፡፴። ህዝቦች በሀብቶቻቸው ምክንያት መኩራት ጀመሩ፣ አልማ ፬፡፮–፯። ህዝቡ እንደ ሀብቱ መሰረት በደረጃ መከፋፈል ጀመሩ፣ ፫ ኄሬ ፮፡፲፪።

ጥበብን እንጂ ሃብትን አትሹ፣ ት. እና ቃ. ፮፡፮ (አልማ ፴፱፡፲፣ ት. እና ቃ. ፲፭፡፮)። የምድር ሃብት ሁሉ ለመስጠት እግዚአብሔር ነው፤ ነገር ግን ኩራትን ተጠንቀቁ፣ ት. እና ቃ. ፴፯፡፴፱።

የዘለአለም ሀብቶች፣ በሰማይ መዝገብ ሰብስቡ፣ ማቴ. ፮፡፲፱–፳፩።

በዘለአለማዊ ህይወት ሀብቶች ጊዜ ጠራጓችሁ፣ ት. እና ቃ. ፵፫፡፳፭። የዘለአለም ሀብትም ለመስጠት የእኔ ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፪ (ት. እና ቃ. ፫፯፡፲፯)።

ሀይል። *ደግምም* ስልጣን፤ ክህነት *ተመልከቱ*

አንድ ነገርን የማድረግ ችሎታ። በአንድ ሰው ወይም በአንድ ነገር ላይ ሀይል መኖር ያን ሰው ወይም ነገር ለመቆጣጠር ወይም ለማዘዝ ችሎታ መኖር ነው። በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ፣ ሀይል ከእግዚአብሔር ሀይል ወይም ከሰማይ ሀይል ጋር የተያያዘ ነው። ይህም ብዙ ጊዜ ለእግዚአብሔር ስራ ፈቃድ ወይም መብት ከሆነው ከክህነት ስልጣን ጋር የተያያዘ ነው።

ኃይሌን እገልጥብህ ዘንድ ስለዚህ አስነሥቼሃለሁ፣ ዘፀአ. ፱፡፲፮። እግዚአብሔር ኃይልን የሚያስታጥቀኝ ነው፣ ፪ ሳሙ. ፳፪፡፴፫። በጎ ነገርን ማድረግ አትከልክል፡ ልታደርግለት የሚቻልህ ሲሆን፣ ምሳ. ፫፡፳፯። በእግዚአብሔር መንፈስ ብርታትንም ተሞልቻለሁ፣ ሚክ. ፫፡፰።

ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ፣ ማቴ. ፳፰፡፲፰። ቃሉ በሥልጣን ነበርና በትምህርቱ ተገረሙ፣ ሉቃ. ፬፡፴፪። እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ፣ ሉቃ. ፳፬፡፴፱። ለተቀበሉት ሁሉ ግን፡ ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፣ ዮሐ. ፩፡፲፪ (ት. እና ቃ. ፲፩፡፴)። መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፣ የሐዋ. ፩፡፰። ከእግዚአብሔር ካልተገኘ በቀር ሥልጣን የለም፣ ሮሜ ፲፣፡፩። ለመዳን በእምነት በእግዚአብሔር ኃይል ተጠብቃችኋል፣ ፩ ጴጥ. ፩፡፣–፩።

በእግዚአብሔር ኃይል ተሞልቻለሁ፣ ፩ ኄሬ ፲፯፡፴፯። ለእኔ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተገልጾልኛል፣ ያዕቆ. ፯፡፲፪። ሰው ከእግዚአብሔር የተሰጠ ታላቅ ኃይል ሊኖረው ይችላል፣ ሞዛያ ፰፡፲፯። በእግዚአብሔር ኃይልና ስልጣን አስተማሩ፣ አልማ ፲፯፡፪–፫። ኄሬ በሃይል እንዲሁም በታላቅ ሥልጣን አገለገለ፣ ፫ ኄሬ ፯፡፲፭–፳ (፫ ኄሬ ፲፭፡፲፱–፳፪)።

ሰው ብዙ ታላላቅ ነገሮችን ለመስራት ሃይል ቢኖረውም፣ ነገር ግን በራሱ ጥንካሬ ቢታበይ፣ እርሱም መውደቅ አለብት፣ ት. እና ቃ. ፫፡፴። መልካም የማድረግ ሀይል ሁሉም ሰው አለው፣ ት. እና ቃ. ፶፰፡፳፯–፳፰። በመልከ ጼዴቅ ክህነት ስነስርዓቶች የአምላክነት ሀይል ይገለጻል፣ ት. እና ቃ. ፹፬፡፲፱–፳፪። የክህነት ሀይል ከሰማይ ሀይሎች ጋር ሳይለያዩ የተያያዙ ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፻፳፭፡፴፱–፴፮።

በእጄም እመራሀለሁ፣ እናም ሀይሌም አንተ ላይ ያርፋል፣ ኦብር. ፩፡፲፰።

ሀይድ፣ ኦርሰን

በዚህ ዘመን በመጀመሪያ ከተጠሩት የአስራ ሁለት ሐዋሪያት ቡድን አባል (ት. እና ቃ. ፳፰፡፩–፫፣ ፳፭፡፲፣ ፻፪፡፫፣ ፻፳፬፡፻፳፰–፻፳፱)። በ፲፰፻፶ (እ.አ.አ.) ቅዱስም ምድርን ለአይሁዳ ህዝቦች መመለስ ከመቀደስ በተጨማሪ፣ ለቤተክርስቲያኗ ብዙ ሚስዮንኖችን ፈጸመ።

ሁለተኛው ሁኔታ። ስጋዊ፣ የሚሞት *ተመልከቱ*

ሁለተኛው ሞት። መንፈሳዊ ሞት *ተመልከቱ*

ሁለተኛው አፅናኝ። አፅናኝ *ተመልከቱ*

ሁለንተና። *ደግምም ታዛዥነት፣ ታዛዥ፣ መታዘዝ ተመልከቱ*

በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ፣ ብዙ ጊዜ በጌታ ወይም በአገልጋዩ የተሰጠ ተግባር፣ የስራ ምደባ፣ ወይም ሀላፊነት።

ይህ የሰው ሁለንተናው ነውና፣ ትእዛዙንም ጠብቅ፣ መክ. ፲፪፡፲፫። እግዚአብሔር ከእንተ ዘንድ የሚሻው ምንድር ነው? ፍርድን ታደርግ ዘንድ ነው፣ ሚክ. ፮፡፰።

ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል፣ የሐዋ. ፭፡፳፱።

ሀላፊነታቸውን እንዲያስታውሱ ለማነሳሳት በመቅሰፍት ተመተው ነበር፣ ሞዛያ ፩፡፲፯።

የሽማግሌዎች የካህናት፣ የመምህራን፣ እና የዲያቆኖች ሀላፊነቶች ተገልጸዋል፣ ት. እና ቃ. ፳፡፴፯–፴፯። የክህነት ባለስልጣኖች የቤተሰብ ሀላፊነቶችን ሁሉ ያከናውኑ፣ ት. እና ቃ. ፳፡፴፣ ፶፩። ከጥምቀት በኋላ አባላት ያሏቸው ሀላፊነቶች ተገልጸዋል፣ ት. እና ቃ. ፳፡፴፰–፴፱። ህዝቦቼ ሀላፊነታቸውን በተመለከት በፍጹም እንዲማሩ ዘንድ ሽማግ

ሌዎቹ ለጥቂት ዘመን ይጠብቁ፣ ት. እና ቃ. ፲፭፡፱–፲፡ እያንዳንዱ ሰው ሀላፊነቱን ይማር፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፶፱–፲፡

ሁሉን የሚያውቅ። *ደግምም* እግዚአብሔር፣ *አምላክ ተመልከቱ*

ስለሁሉም ነገሮች እውቀት የማግኘት መለኮታዊ ባህሪይ (ማቴ. ፮፡፰፤ ፪ ኔፊ ፪፡፳፬)።

ሁሉን የሚገዛ። *ደግምም* እግዚአብሔር፣ *አምላክ ተመልከቱ*

ሁሉንም ሀይል የሚኖረው መለኮታዊ ባህሪይ (ዘፍጥ. ፲፰፡፲፬፤ አልማ ፳፮፡፴፭፤ ት. እና ቃ. ፲፱፡፩–፫)።

ሄሮድስ

በኢየሱስ ክርስቶስ ዘመን አካባቢ በይሁዳ ውስጥ መሪዎች የነበሩ ቤተሰቦች። በብዙዎቹ የአዲስ ኪዳን ድርጊቶች እነርሱ አስፈላጊ ሰዎች ነበሩ። ቤተሰቡ የተጀመረው ስለአዳኝ መወለድ በፈራው (ማቴ. ፪፡፫) እና በቤተልሔም ህጻናት እንዲገደሉ ትእዛዝ በሰጠው በታላቁ ሄሮድስ ነበር። ወንድ ልጅ ቹም አርስጣባሉ፣ ሄሮድስ ፊልጶስ (ማቴ. ፲፬፡፫፤ ማር. ፮፡፲፯)፤ የአራተኛው ክፍል ገዥ ሄሮድስ አን ቲጳስ (ማቴ. ፲፬፡፩፤ ሉቃ. ፱፡፯፤ ደግሞም ንጉስ ሄሮድስ ተብሎ የሚታወቀው፣ ማር. ፮፡፲፬)፤ አር ኪሊዎስ (ማቴ. ፪፡፳፪)፤ እና ፊልጶስ፣ የአራተ ኛው ክፍል ገዥ (ሉቃ. ፫፡፩) ነበሩ። ሄሮድስ አግሪጳ ቀዳማዊ (የሐዋ. ፲፪፡፩–፳፫) እና እህቱ ሄሮድያዳ (ማቴ. ፲፬፡፫፤ ማር. ፮፡፲፯) የአርስጣባሉ ልጆች ነበሩ። ሄሮድስ አግሪጳ ቀዳማዊም በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተጠቀሱ ብዙ ልጆች ነበሩት፣ እነርሱም ሄሮድስ አግሪጳ ካልዕ (የሐዋ. ፳፭፡፲፫)፣ በርኒቄ (የሐዋ. ፳፭፡፲፫)፣ እና ድሩሲላ፣ የፊልክስ ባለ ቤት (የሐዋ. ፳፬፡፳፬) ነበሩ።

ሄሮድያዳ

በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሄሮድስ አግሪጳ እህት። ከአጎቷ ከሄሮድስ ፊልጶስ ጋር የተጋባች ነበረች፣ በእርሱም ሰሎሜ የምትባል ሴት ልጅ ወልዳ ነበር። እርሷ እና ሰሎሜ መጥምቁ ዮሐንስን ለማስቀላት አደሙ (ማቴ. ፲፬፡፫–፲፩)።

ህሊና። *ደግምም* ብርሀን፣ የክርስቶስ ብርሀን *ተመልከቱ*

በሁሉም ሰዎች ውስጥ ከሚገኘው የክርስቶስ ብር ሀን የሚመጣው፣ በውስጥ የሚሰማ የትክክለኛነት ወይም ትክክል ያለመሆን ስሜት(ሞሮኒ ፯፡፲፯)። ትክክልን ወይም ትክክል ያልሆነን ለይቶ ለማ ወቅ የሚያስችል ችሎታ ለእያንዳንዱ ሰው በተሰ ጠው በክርስቶስ ብርሀን ምክንያት አለን(ት. እና ቃ. ፹፬፡፴፯)። ይህ ችሎታ ህሊና ይባላል። ይህም ሲኖ ረን ሀላፊነት ያላቸው ያደርገናል። እንደ ሌሎች አይ ነት ችሎታዎች፣ ህሊናዎቻችን በኃጢያት ወይም በትክክል ባለመጠቀም ምክንያት ሊደነድኑ ይች ላሉ።

ጻህፊዎችና ፈሪሳውያን ህሊናቸው ወቀሳቸው፣ ዮሐ. ፰፡፱። ለእነርሱ ሕሊናቸው መሰከረላቸው፣ ሮሜ ፪፡፲፭–፲፮። ሀይማኖት የሚክዱት የገዛ ሕሊ ናቸው አቃጠሉ፣ ፩ ጢሞ. ፬፡፪።

ሰዎች መጥፎን ከጥሩው መለየትን ለማወቅ በብ ቃት ተምረዋል፣ ፪ ኔፊ ፪፡፭ ንጉስ ቢንያም በእግ ዚአብሔር ፊት ንጹህ ህሊና አለው፣ ሞዛያ ፪፡፲፮። ኔፋውያን የህሊና ሰላም ኖሯቸው በደስታ ተሞል ተው ነበር፣ ሞዛያ ፬፡፫። ዚኤዝሮም እናም ነፍሱ በጥፋቱ እውቀት የተነሳ መሰቃየት ጀመረች፣ አልማ ፲፬፡፮። በፍላጎታችን መሰረት የደስታ ወይም የጸጸት ህሊና ተሰጥቶናል፣ አልማ ፳፱፡፭። ቅጣት እና ጻድቅ ህግ የጸጸት ህሊናን ያመጣል፣ አልማ ፴፪፡፲፳። እያንዳንዱ ሰው ጥሩን ከመጥፎ እን ዲያውቅ ዘንድ የክርስቶስ መንፈስ ተሰጥቶታል፣ ሞሮኒ ፯፡፲፯።

እያንዳንዱ የህሊና ነጻ ጥቅም ይኑረው፣ ት. እና ቃ. ፻፴፬፡፪። እና ለሁሉም ሰዎች ከማና ደድ ንጹ ህሊና አለኝ፣ ት. እና ቃ. ፻፴፭፡፬።

እግዚአብሔርን ኅሊናችን እንደሚመራን የማም ለክ መብት እንዳለን እናረጋግጣለን፣ እ.አ. ፩፡፲፩።

ህልም። *ደግምም ራዕይ ተመልከቱ*

በምድር ላይ እግዚአብሔር ፈቃዱን ለወንዶ ችና ለሴቶች የሚሰጥበት አንድ መንገድ። ነገር ግን፣ ሁሉም ህልሞች ራዕዮች አይደሉም። የተነሳሱ ህል ሞች የእምነት ፍሬ ናቸው።

ህልምም አለመ፤ እነሆም መሰላል ሰማይ ደርሶ ነበር፣ ዘፍጥ. ፳፰፡፲፪። ዮሴፍም ህልምን አለመ፣ ዘፍጥ. ፴፯፡፭። ጌታ በራዕይ ይገልጥለታል፣ ዘኁል. ፲፪፡፮። ናቡከደነጾር ህልምን አለመ፣ ዳን. ፪፡፩–፫። ሽማግሌዎቻችሁም ህልምን ያልማሉ፣ ኢዩ. ፪፡፳፰ (የሐዋ. ፪፡፲፯)።

የጌታ መልአክ በሕልም ታየው፣ ማቴ. ፩፡፳ (ማቴ. ፪፡፲፫)።

ሌሂ በህልም ያያቸውን ብዙ ነገሮች ፅፏል፣ ፩ ኔፊ ፩፡፲፯። ሌሂ ህልምን አለመ፣ ፩ ኔፊ ፰።

ህብረት። የሚስጥር ስብሰባ *ተምልከቱ*

ህያው ማድረግ። *ደግምም ትንሳኤ ተመልከቱ*

ህያው ማድረግ፣ ከሞት ማስነሳት፣ ወይም በእ ግዚአብሔር ፊት ለመገኘት እንዲችል ሰውን መቀ የር።

እግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን፣

ኤፌ. ፪፡፬–፭ (ቁላ. ፪፡፮፣ ፲፪–፲፫)። ክርስቶስ በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ፣ ፮ ጴጥ. ፫፡፲፰ (ት. እና ቃ. ፲፱፡፲–፲)።

በእግዚአብሔር መንፈስ የተነሳሱ ካልሆኑ በስ ተቀር፣ በስጋ እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም፣ ት. እና ቃ. ፴፯፡፲፩። የነፍስ ቤዛነትም ሁሉ ንም ነገሮች ህይወት በሚሰጠው ነው፣ ት. እና ቃ. ፸፫፡፲–፲፯። ህያው የሆኑት፣ ከክርስቶስ ጋር ይነጠቃሉ፣ ት. እና ቃ. ፸፫፡፶፯።

አዳም በውስጥ ሰውነትም ህይወት ተሰጠው፣ ሙሴ ፮፡፴፭።

ህያው ውሀ። *ደግሞም ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልከቱ*

የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስና የትምህርቱ ምልክቶች። ስጋዊ ሰውነትን ለመደገፍ ውሀ አስፈላጊ እንደሆነ፣ አዳኝ እና ትምህርቶቹ (ህያው ውሀ) ለዘለአለም ህይ ወት አስፈላጊ ናቸው።

ውኃውንም ከመድኃኒት ምንጮች በደስታ ትቀዳላችሁ፣ ኢሳ. ፲፪፡፫። እኔን የሕያውን ውኃ ምንጭ ትተውኛል፣ ኤር. ፪፡፲፫።

እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠማ ሁሉ ግን ለዘላለም አይጠማም፣ ዮሐ. ፬፡፲–፲፩። ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠማ፣ ዮሐ. ፯፡፴፯።

የብረት በትር ወደ ህይወት ውሃዎች ምንጭ ይመ ራል፣ ፮ ኔፊ ፲፩፡፳፭።

ከህይወት ውሃ በነፃ ጠማ፣ ት. እና ቃ. ፲፡፸፯። ትእዛዛቴ ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የውኃ ምንጭ ይሆናል፣ ት. እና ቃ. ፸፫፡፸፫።

ህያው፣ ዘለአለማዊ ህይወት። *የማይሞት፣ አለሟችነት ተመልከቱ*

ህይወት። *ደግሞም ብርሀን፣ የክርስቶስ ብርሀን፣ የዘለዓለም ህይወት ተመልከቱ*

በእግዚአብሔር ሀይል በኩል ሊሆን የቻለ ስጋዊና መንፈሳዊ አኗኗር።

ዛሬ በፊትህ ሕይወትንና መልካምነትን፥ ሞት ንና ክፋትን አኑሬአለሁ፣ ዘዳግ. ፴፡፲፭–፳። የሕ ይወትን መንገድ አሳየኸኝ፣ መዝ. ፲፮፡፲፩። ጽድቅ ንና ምሕረትን የሚከተል ሕይወትን ያገኛል፣ ምሳ. ፳፩፡፳፩።

ነፍሱን የሚያገኝ ያጠፋታል፥ ነፍሱንም ስለ እኔ የሚያጠፋ ያገኛታል፣ ማቴ. ፲፡፴፱ (ማቴ. ፲፮፡፳፭፣ ማር. ፰፡፴፭፣ ሉቃ. ፱፡፳፬፣ ፲፯፡፴፫)። የሰው ልጅ የሰውን ነፍስ ሊያድን እንጂ ሊያጠፋ አልመጣም፣ ሉቃ. ፱፡፶፮። በእርሱ ሕይወት ነበ ረች፥ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች፣ ዮሐ. ፩፡፬። በእርሱ የሚያምን ከሞትም ወደ ሕይወት ይሻገራል እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም፣ ዮሐ. ፭፡፳፬። እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፣ ዮሐ. ፲፬፡፮። በዚች ሕይወት ብቻ ክርስቶስን ተስፋ ያደረግን ከሆነ፣ ከሰው ሁሉ ይልቅ ምስኪኖች ነን፣ ፮ ቆሮ. ፲፭፡፲፱–፳፪። እግዚአብሔርን መምሰል ግን የአሁንና የሚመጣውን ሕይወት ተስፋ አለው፣ ፮ ጢሞ. ፬፡፰።

ልጆቻችን በክርስቶስ የሆነውን ህይወት ወደፊት ይመልከቱ፣ ፪ ኔፊ ፳፭፡፳፫–፳፯። ይህ ጊዜ ለሰዎች እግዚአብሔርን ለመገናኘት የዝግጅት ወቅት ነው፣ **አልማ** ፴፬፡፴፪ (አልማ ፲፪፡፳፬)። እኔ የአለም ብርሃን እናም ህይወት ነኝ፣ ፲ ኔፊ ፱፡፲፰ (ሞዛያ ፲፯፡፱፣ ፲ ኔፊ ፲፭፡፲፭፣ ኤተር ፬፡፲፪)።

በህይወትም ይሁን በሞት፣ ታማኝ የሆኑት የተ ባረኩ ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፯፡፭። እግዚአብሔር ንና የላከውን ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት፣ ት. እና ቃ. ፲፴፪፡፳፰።

የሰውን ህያውነት እና ዘለአለማዊ ህይወት አምጥ ቶም የማሳለፍ ስራዬ እና ክብሬ ይህም ነው፣ ሙሴ ፩፡፴፱።

ህይወት መስጠት። ህያው ማድረግ *ተመልከቱ*

ህገ መንግስት። *ደግሞም ህግ፣ መንግስት ተመልከቱ*

በትምህርት እና ቃልኪዳኖች ውስጥ፣ "ህገ መን ግስት" የሚጠቀሰው ወንጌልን ዳግም ለመመለስ መንገድን ለማዘጋጀት በመለኮታዊነት የተነሳሳውን የዩናይትድ ስቴትስን ህገ መንግስትን ነው።

ከህገ መንግስት ጋር ጓደኝነት ይኑር፣ ት. እና ቃ. ፶፯፡፩–፮። ጌታ ህገ መንግስት እንዲመሰረት አደ ረገ፣ ት. እና ቃ. ፭፩፡፫፯፣ ፹።

ህግ። *ደግሞም መባረክ፣ የተባረከ፣ በረከት፣ ታዛዥነት፣ ታዛዥ፣ መታዘዝ፣ የሙሴ ህግ፣ የእግዚአብሔር ትእዛዛት ተመልከቱ*

በሰማይ ውስጥ እናም በምድር ውስጥ ሁሉም በረ ከቶች እና ቅጣቶች የሚመረኮዙባቸው የእግዚአብ ሔር ትእዛዛት ወይም ደንብ። የእግዚአብሔርን ህግ የሚያከብሩ በተስፋ ቃል የተሰጡትን በረከቶች ይቀ በላሉ። ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ ሰዎች ለምድር ህግጋት ታዛዥ መሆን፣ ማክበር፣ እና መደገፍ እንዳለባቸው አስተምሯል (እ.አ. ፩፡፲፪)።

የሙሴ ህግ ወንዶችን እና ሴቶችን ወደ ክርስ ቶስ የሚያመጣ የመዘጋጃ ህግ ነበር። ይህም የመ ገደቢያ፣ መደረግ የሚገባውን ማዘዣ፣ እና የስነስ ርዓቶች ህግ ነበር። ዛሬ የሙሴን ህግ ያሟላው የክ ርስቶስ ህግ የወንጌሉ ሙላት ወይም "ጎዳ የሚያወ ጣው ፍጹሙ ሕግ" ነው (ያዕ. ፩፡፳፭)።

እግዚአብሔር ለአዳም ትእዛዛትን ሰጠ፣ ዘፍጥ. ፩፡፳፰፣ ፪፡፲፮–፲፯። እግዚአብሔር ለኖህ ህግጋ ትን ሰጠ፣ ዘፍጥ. ፱፡፩። የእግዚአብሔር ሕግ ፍጹም ነው፤ ነፍስን ይመልሳል፣ መዝ. ፲፱፡፯።

እግዚአብሔር ሕግን ሰጪያችን ነው፣ ኢሳ. ፴፫፡፳፪።

ሕግን የሚሰጥና የሚፈርድ አንድ ነው፣ ያዕ. ፬፡፲፪።

ህግ ባልተሰጠበት ቅጣት የለም፣ ፪ ኔፊ ፱፡፳፭። ህግ ተሰጥቷል፣ አልማ ፶፪፡፲፯–፳፪። ሰዎች በህግ መሰረት ይፈረድባቸዋል፣ አልማ ፶፪፡፳፫። ክር ስቶስ ህግ ነው፣ ፫ ኔፊ ፲፭፡፱። ሁሉም ህግጋት መንፈሳዊ ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፴፬–፴፭። ጆሴፍ ስሚዝ የቤተክርስቲያናን ህግ በራዕይ ተቀበለ፣ ት. እና ቃ. ፶፪። የእግዚአብሔርን ህግጋትን የሚጠብቅ የምድርን ህግጋት የመጣስ ፍላጎት አይኖረውም፣ ት. እና ቃ. ፻፳፡፲፭። የክርስቶስ ብርሀን ሁሉም ነገሮች የሚገዙበት ህግ ነው፣ ት. እና ቃ. ፹፰፡፲–፲፫። ለሁሉም ነገሮች ህግ ሰጥቷል፣ ት. እና ቃ. ፹፰፡፶፪–፶፫። ሰዎች የምድርን ህግ ያክብሩ፣ ት. እና ቃ. ፻፳፡፱–፲፩። በረከት ከእግዚአብሔር የምናገኘውም በተመሮከዘበት በእግዚአብሔር ህግ ታዛዥነት ነው፣ ት. እና ቃ. ፻፶፡፭–፲፩። ቤተክርስቲያኗ የህዝባዊ ህግን በሚመለከት ስላላት እምነት አወጀች፣ ት. እና ቃ. ፻፶፩።

የወንጌሉን ህግጋትና ስነ ስርዓቶችን በማክበር፣ የሰው ዘሮች ሁሉ መዳን ይችላሉ፣ ኤ.አ. ፩፡፫።

ሆሳዕና

“እባክህ አድነን” የሚል ትርጉም ያለው እና በሙገሳና በአምልኮት የሚጠቀሙበት የዕብራውያን ቃል።

ጌታ እስራኤልን ወደ ቃል ኪዳን ምድር ያዳነበትን በሚያከብሩበት የዳስ በዓል፣ ሰዎች የመዝሙር ፻፲፰ ቃላትን እየደጋገሙ ይላሉ እናም ዘንባባን ያውለበልባሉ። ጌታ ወደ ኢየሩሳሌም በድል በገባበት ጊዜ፣ ህዝቦቹ “ሆሳዕና” በማለት ጮሁ እናም ኢየሱስን እየጋለበ እንዲሄድበት ዘንባባ ቅርንጫፎችን አነጠፉ፣ በዚህም ኢየሱስ እስራኤልን በጥንት ያዳነ አንድ ጌታ እንደሆነ እንደገባቸው አሳዩ (መዝ. ፻፲፰፡፳–፳፭፣ ማቴ. ፳፩፡፱፣ ፲፭፣ ማር. ፲፩፡፱–፲፣ ዮሐ. ፲፪፡፲፫)። እነዚህ ህዝቦች ክርስቶስን ለረጅም ጊዜ ይጠበቅበት እንደነበረው መሲሕ አወቁት። *ሆሳዕና* የሚባለው ቃል በሁሉም ዘመናት መሲሕ የሚከበርበት ሆኗል (፩ ኔፊ ፲፭፡፲፣ ፫ ኔፊ ፲፭፡፲፬–፲፯)። የሆሳዕና ጩኸት በከርትላንድ ቤተ መቅደስ በሚቀደስ ጊዜም ተጨምሯል (ት. እና ቃ. ፻፹፡፫፹፱) እና አሁንም የእዚህ ዘመን ቤተመቅደሶች የመቀደስ ክፍል ነው።

ሆሴዕ

በሰሜን የእስራኤል መንግስት ውስጥ በጀሮቦአም ካልዕ ዘመነ መንግስት መጨረሻ አካባቢ የተነበየ የብሉይ ኪዳን ነቢይ። በእስራኤል ኃጢያት ውጤት በሆነው በሀገር መዳከም እና ውድመት ጊዜ ነበር የኖረው።

ትንቢተ ሆሴዕ፣ የመፅሐፉ መሰረታዊ ጭብጥ መልእክት እግዚአብሔር ለህዝቡ ስላለው ፍቅር ነው። ግሰጻዎቹ ሁሉ የሚመጡት በፍቅር ነው፣ እናም የእስራኤል ዳግም መመለስም በፍቅሩ ምክንያት ነው (ሆሴ. ፪፡፲፱፣ ፲፬፡፬)። በማነጻጸርም፣ ሆሴዕ የእስራኤልን ክህደትና ታማኝ አለመሆንን አሳየ። ነገር ግን እግዚአብሔር ስለእስራኤል የመጨረሻ ቤዛነት በጉጉት ይጠብቃል (ሆሴ. ፲፩፡፲፪–፲፬፡፱)።

ለሙታን ደህንነት

ደግሞም የመታሰቢያ መፅሐፍ፣ የቤዛነት ዕቅድ፣ የትውልድ ሐረግ፣ ደህንነት ተመልከቱ

ይህም የሚያድኑ የወንጌል ስነስርዓዮችን ሳይቀበሉ ለሞቱት እነዚህን ስነስርዓቶች ብቁ በሆኑ ህያው የቤተክርስቲያን አባላት ለእነርሱ በቤተመቅደስ ውስጥ የማከናወን እድል ነው። ሙታን ወንጌልን በመንፈስ አለም ውስጥ ተምረዋል እናም በስጋዊነት የተከናወነላቸውን ስነስርዓቶች መቀበልን ይችላሉ።

ታማኝ የቤተክርስቲያኗ አባላት የሚያድኑት ስነስርዓቶች ለእነርሱ ይከአንወንላቸው ዘንድ የቅድመ አባቶቻቸውን ስም እና የልደት ቀን ለማወቅ የቤተሰብን ታሪክ ይፈትሻሉ እናም ያዘጋጃሉ።

የተጋዙትንም፣ ውጡ በላቸው፣ ኢሳ. ፵፱፡፱ (ኢሳ. ፷፡፡፣ ፷፪፡፩ ፡ ፡ ኔፊ ፳፭፡፱)። ለተማረኩትም ነጻነትን ተናገር፣ ኢሳ. ፷፩፡፩ (ሉቃ. ፬፡፲፰)። እርሱ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች ይመልሳል፣ ሚል. ፬፡፭–፮ (፫ ኔፊ ፳፭፡፭–፮፣ ት. እና ቃ. ፲፪፡፲፣ ፲፫–፲፯)።

ሙታን የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ ይሰማሉ፣ ዮሐ. ፭፡፳፭። ስለ ሙታን የሚጠመቁ ስለ ምን ድር ነው፣ ፩ ቆሮ. ፲፭፡፳፱። ክርስቶስ በሙታን መካከል ሰበከ፣ ፩ ጴጥ. ፫፡፲፰–፳። ስለዚህ ምክንያት ወንጌል ለሙታን ደግሞ ተሰብኮላቸው ነበር፣ ፩ ጴጥ. ፬፡፮።

ወልድ በወኅኒ ውስጥ የነበሩት የሰዎች ነፍሶች ጎበኘ፣ ት. እና ቃ. ፷፯፡፷፫። ከዚያም ለእነርሱ የተዘጋጀውን የእስር ቤት ክፍልም የተቀበሉት ቤዛነትም ይመጣል፣ ት. እና ቃ. ፻፳፡፲፬። እነርሱ ቅዱሳኔ ለሙታን ይጠመቁ ዘንድ፣ በምድርም ላይ የማጥመቂያ ገንዳ የለምና፣ ት. እና ቃ. ፲፳፬፡፳፱። ወንጌሉን ይቀበሉት የነበሩት፣ የሞቱት ሁሉ የእግዚአብሔር ሰለስቲያል መንግስት ወራሾች ይሆናሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፱፯፡፲–፲። የእግዚአብሔር ልጅ ታማኝ ለነበሩት ለታሰሩት ነጻነትን በማወጅ መጣ፣ ት. እና ቃ. ፲፱፯፡፲፰።

በእስር ቤት የነበሩትም ሁሉ መንፈሶች መጡ፣ ሙሴ ፗ፡ ፱ፗ።

ለምን። *ደግሞም ጸሎት ተመልከቱ*

እግዚአብሔርን ለልዩ ውለታ መጠየቅ፣ ጥያቄ ማቅረብ፣ ወይም አቤቱታ ማቅረብ።

ለምኑ፡ ይሰጣችሁማል፣ ማቴ. ፯፡ ፯። ከእና ንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው፣ . . .እግዚአብ ሔርን ይለምን፣ ያዕ. ፩፡ ፭ (ጆ.ስ.—ታ. ፩፡ ፯–፳)።

በእምነት ጠይቁኝ፣ ፮ ኔፊ ፲፭፡ ፲፩። መረዳት ካልቻላችሁ፣ ይህም ስላልጠየቃችሁ ነው፣ ፪ ኔፊ ፴፪፡ ፱። ከልባችሁ ጠይቁ፣ ሞዛያ ፱፡ ፲። እግዚአብ ሔር ትክክለኛ የሆነውን ማንኛውንም ነገር በእምነት የምትጠይቁትን ይሰጣችኋል፣ ሞዛያ ፱፡ ፳፩። እነ ዚህ ነገሮች ሀሰት እንደሆኑ እግዚአብሔርን ጠይቁ፣ ሞሮኒ ፲፡ ፱።

ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ይወዳሉ፤ ስለዚህም እኔን አይጠይቁም፣ ት. እና ቃ. ፲፡ ፳፩። እግዚአ ብሔርን ስለሁሉም ነገሮች እንድትጠይቁት ታዝዛ ችኋል፣ ት. እና ቃ. ፴፯፡ ፯።

ለምፅ

በብሉይ ኪዳን እና በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተና ገሩበት መጥፎ የቆዳ በሽታ። ከሙሴ (ዘፀአ. ፱፡ ፯–፯)፣ ከእህቱ ማርያም (ዘኁል. ፲፪፡ ፲)፣ ከናዕማን (፪ ነገሥ. ፭)፣ እና ከንጉስ ዖዝያን (፪ ዜና ፳፮፡ ፲፱–፳፩) በተጨማሪ፣ የመፅሀፍ ቅዱስ ብዙ ታዋቂ ሰዎች አንዳንዴ የተሰቃዩበት ነው።

ኢየሱስ ብዙ ለምጻም ሰዎችን ፈወሰ፣ ማቴ. ፰፡ ፪–፱ (ማር. ፩፡ ፴–፴፭፣ ሉቃ. ፭፡ ፲፪–፲፭፣ ፣ ኔፊ ፲፯፡ ፯–፱)። ኢየሱስ አስር ለምጻሞችን ፈወሰ፣ ሉቃ. ፲፯፡ ፲፩–፲፱።

ለታመሙት አገልግሎት መስጠት። *ደግሞም መቀባት፣ መፈወስ፣ ፈውሶች፣ እጅን መጫን፣ ክህነት፣ ዘይት ተመልከቱ*

የተቀደሰ ዘይት በመጠቀም፣ የመልከ ጼዴቅ ክህ ነት ያላቸው ወንዶዎች ለታመሙት የሚሰጡት በረ ከት።

እጅህን ጫንባት፣ ማቴ. ፱፡ ፲፰። ኢየሱስ በጥ ቂቶች ድውዮች ላይ እጁን ጭኖ ፈወሳቸው፣ ማር. ፮፡ ፭። የክርስቶስ ሀዋሪያት ብዙ ድውዮችንም ዘይት እየቀቡ ፈወሱአቸው፣ ማር. ፮፡ ፲፫። ሽማግሌዎች ድውዮችንም ዘይት ቀብተው ይፈውሳሉ፣ ያዕ. ፭፡ ፲፬–፲፭።

ይህን የሚፈልጉት ካልጠየቁህ በስተቀር፣ የታ መሙትን አትፈውስ፣ ት. እና ቃ. ፳፬፡ ፲፣–፲፪። ሽማግሌዎች በታመሙት ላይ እጆቻቸውን ይጫኑ፣ ት. እና ቃ. ፴፪፡ ፴፬። በታመሙትም ላይ እጆች ህን ጫን፣ እናም ይድናሉ፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡ ፱።

ለፍርድ መቅረብ፣ *ፍርድ ማድረግ*። ዳኛ፣ ፍርድ *ተመልከቱ*

ሉቃስ። *ደግሞም ወንጌሎች፤ የሐዋርያት ስራ ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሉቃስ ወንጌልና የሐዋር ያት ስራ ጸሀፊ እና የጳውሎስ የሚስዮን የጉዞ ጓደኛ ነው። ለግሪክ ወላጆች የተወለደ እና ባለ መድኃኒት ነበር (ቁላ. ፬፡ ፲፬)። ሉቃስ በደንብ የተማረ ነበር። በጢሮአዳ ከጳውሎስ ጋር ሲገናኝ እራሱን እንደ ሐዋሪያ ጳውሎስ የጉዞ ጓደኛ አስተዋወቀ (የሐዋ. ፲፮፡ ፣–፲፩)። ጳውሎስ ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ኢየ ሩሳሌም በተጓዘበት ጊዜ በፊልጵስዩስ ሉቃስ ከጳ ውሎስ ጋር ነበር (የሐዋ. ፳፡ ፮)፣ እናም ወደ ሮሜ እስከሚደርሱ ድረስ አብረው ነበሩ። ጳውሎስ ለሁ ለተኛ ጊዜ በሮሜዎች በታሰረበት ጊዜ ሉቃስ ከእ ርሱ ጋር ነበር (፪ ጢሞ. ፬፡ ፲፩)። በባህል እንደሰ ማዕት ሞተ ይባላል።

የሉቃስ ወንጌል፣ ስለኢየሱስ ክርስቶስ እና ስለ ስጋዊ አገልግሎቱ በሉቃስ የተጻፈው ታሪክ። የሐ ዋርያት ስራ መፅሐፍ ከሉቃስ ወንጌል የሚቀጥል ነው። ሉቃስ ኢየሱስን እንደ አይሁዶች እና አህ ዛብ አዳኝ በማሳየት፣ የኢየሱስ አገልግሎት ታሪ ክን በግልፅ ጻፈ። ስለኢየሱስ ትምህርቶችና ስለ ድርጊቶቹም ብዙ ጻፈ። ገብርኤል ዘካርያስን እና ማርያምን ስለጎበኘበት (ሉቃ. ፩)፣ ህጻኑ ኢየሱ ስን በእረኞች መጎብኘት (ሉቃ. ፪፡ ፰–፲፰)፣ ኢየ ሱስ በአስራ ሁለት አመቱ በቤተመቅደስ የነበረበት (ሉቃ. ፪፡ ፵፩–፵፪)፣ ለሰባዎች ስለተሰጠው ሀላፊ ነት እና መላክ (ሉቃ. ፲፡ ፩–፳፬)፣ ስለኢየሱስ ደም እንዳላበው (ሉቃ. ፳፪፡ ፵፬)፣ በመስቀል ላይ ኢየ ሱስ ከሌባው ጋር ስለተነጋገረው (ሉቃ. ፳፫፡ ፴፱–፵፣)፣ እና ኢየሱስ ከትንሳኤው በኋላ አሳና ማር ስለመብላቱ (ሉቃ. ፳፬፡ ፵፪–፵፣)፣ ታሪኮች በሉቃስ ውስጥ ብቻ እናገኛለን።

በሉቃስ ወንጌል ውስጥ የተገለጹትን የአዳኝ ህይ ወት ድርጊቶች ዝርዝር፣ የወንጌሎች ስምምነትን ተመልከቱ።

ሊምሂ። *ደግሞም ኖኅ፣ የዘኒፍ ልጅ ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ በኔፊ ምድር ውስጥ የነበረ ጻድቅ የኔፋውያን ንጉስ፤ እርሱም የንጉስ ኖህ ልጅ ነበር (ሞዛያ ፯፡ ፯–፱)። ንጉስ ሊምሂ እግዚአብ ሔርን ለማገልገል ቃል ኪዳን ገባ (ሞዛያ ፳፩፡ ፴፪)። ህዝቡን ከላማናውያን ባርነት አወጣ እናም ወደ ዛራሔምላ እንደገና መለሰ (ሞዛያ ፳፪)።

ሊቀ ካህን። *ደግሞም አሮናዊ ክህነት፤ የመልከ ጼዴቅ ክህነት ተመልከቱ*

በክህነት ስልጣን ውስጥ አንዱ ሀላፊነት። ቅዱሣት መጻህፍት “ሊቀ ካህንን” በሁለት አስ

ተያየት ይናገሩበታል፥ (፩) በመልከ ጼዴቅ ክህነት ውስጥ አንዱ ሀላፊነት፣ እና (፪) በሙሴ ህግ ስር፣ የአሮናዊ ክህነት አመራር ባለስልጣን።

የመጀመሪያው አስተያየት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ታላቁ ሊቀ ካህን ያመለክታል። አዳም እና የአባት አለቆች ሁሉ ሊቀ ካህናት ነበሩ። ዛሬ፣ ሶስት ሊቀ ካህናት የቤተክርስቲያኗን አመራር ይመሰርታሉ እናም የሁሉም የክህነት ባለስልጣኖች እና የቤተክርስቲያን አባላት መሪዎች ናቸው። ዛሬ ቤተክርስቲያን ውስጥ ተጨማሪ ብቁ ወንዶች ትክክለኛ ሲሆኑ እንደ ሊቀ ካህናት ይሾማሉ። ሊቀ ካህናት በኤጲስ ቆጶሳት መጠራት፣ መለየት፣ እና መሾም አለባቸው(ት. እና ቃ. ፳፯፡፲፱፣ ፲፯፡፳፱–፴፩)።

በሁለተኛው አስተያየት፣ በሙሴ ህግ መሰረት፣ የአሮናዊ ክህነት አመራር ባለስልጣን ሊቀ ካህን ተብሎ ይጠራል። ይህ ስልጣን በዘር የሚወረስ እና በአሮን ቤተሰብ መካከል በበኩር በኩል የሚመጣ ነበር፣ አሮን እራሱም የአሮናዊ ስርዓት የመጀመሪያ ሊቀ ካህን ነበር (ዘፀአ. ፳፰–፳፱፣ ዘሌዋ. ፰፣ ት. እና ቃ. ፹፬፡፲፣ ፲፰)።

መልከ ጼዴቅም የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበረ፣ ዘፍጥ. ፲፬፡፲፰ (አልማ ፲፫፡፲ፀ)።

ሊቀ ካህናት ከአለም መመስረት ጀምሮ ተጠርተዋል እናም ተዘጋጅተዋል፣ **አልማ** ፲፫፡፩–፲።

ሊቀ ካህናት በመንፈሳዊ ነገሮች ያስተዳድራሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፲፣ ፲፪፣ ፲፯።

ሊያሆና

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ ሁለት መጠቆሚያዎች የነበረው እናም ደግሞም እንደ አቅጣጫ መለያ መሳሪያ ለሌሂና ጻድቅ ለሆኑት ተከታዮቹ መንፈሳዊ መመሪያ የሚሰጥ የነሀስ ኳስ። ጌታ ሊያሆናውን ሰጠ እናም በዚህ በኩል መመሪያዎችን ሰጠ።

ሌሂ ሁለት እንዝርቶች የነበሩት ሌሂ እና ቤተሰቡ መሄድ ያለባቸውን አቅጣጫ የሚጠቁም በነሐስ የተሰራ ክብ ኳስ አገኘ፣ **፤ ኔፊ** ፲፮፡፲። ኳሱ የሚሰራው ለእነርሱ በሚሰጣቸው እምነትና ትጋት መሰረት ነው፣ **፤ ኔፊ** ፲፮፡፳፰–፳፱ (አልማ ፴፯፡፵)። ቢን ያም ኳሱን ለሞዛያ ሰጠ፣ **ሞዛያ** ፩፡፲፮። ኳስ ወይንም ጠቋሚ ሊያሆና ይባላል፣ **አልማ** ፴፯፡፴፡ ሊያሆና ከክርስቶስ ቃል ጋር ተነጻጽሯል፣ **አልማ** ፴፯፡፴፣–፴፭።

የመፅሐፈ ሞርሞን ሶስት ምስክሮችለሌሂ የተሰጠውን ጠቋሚ ይመለከታሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፩።

ላማናውያኑ ሳሙኤል

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ ከአዳኝ መወለድ በፊት ኔፋውያንን እንዲያስተምር እና እንዲያስጠነቅቅ በጌታ የተላከ ላማናውያን ነቢይ። ሳሙኤል ከኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ እና መሞት ጋር ግንኙነት ስላላቸው ምልክቶች እና ስለኔፋውያን ጥፋት ተነበየ (ሔለ. ፲፣–፲፮)።

ላማናውያን፡ *ደግምም ላማን፣ መፅሐፈ ሞርሞን፣ ኔፋውያን ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ ያሉ ህዝቦች፣ ብዙዎቹ የሌሂ የመጀመሪያ ልጅ የላማን ትውልዶች ነበሩ። በኔፊ እና በትውልዶቹ የማይገባ ነገሮች እንደተደረጉባቸው ይሰማቸው ነበር (ሞዛያ ፣ ፲፡፲–፲፮)። በዚህም ምክንያት፣ በኔፋውያን ላይ አመጹ እናም ብዙም ጊዜ የወንጌል ትምህርቶችን አስወገዱ። ነገር ግን፣ ከኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ ከትንሽ ጊዜ በፊት፣ ላማናውያን ወንጌልን ተቀበሉ እናም ከኔፋውያን ይልቅ ጻድቅ ነበሩ (ሔለ. ፮፡፴፩–፴፮)። ክርስቶስ አሜሪካን ከጎበኘ ከሁለት መቶ አመት በኋላ፣ ላማናውያን እና ኔፋውያን ክፉዎች ሆኑ እናም እርስ በራስ መዋጋት ጀመሩ። በ፬፻ ዓ.ም. አካባቢ፣ ላማናውያን የኔፋውያን ህዝቦችን በሙሉ አጠፉ።

ላማናውያን የኔፋውያን ዘሮች አሸነፉ፣ **፤ ኔፊ** ፲፪፡፲፱–፳፡ ላማናውያን ኔፋውያንን ጠሉ፣ **፪ ኔፊ** ፭፡፲፩፡ ላማናውያን ለኔፋውያን እንደ ጅራፍ ይሆናሉ፣ **፪ ኔፊ** ፭፡፳፭፡ መፅሐፈ ሞርሞን ለላማናውያን የቅድመ አባቶቻቸውን እና የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል እውቀቶችን ዳግም ይመልስላቸዋል፣ **፪ ኔፊ** ፴፡፣–፤ (የመፅሐፈ ሞርሞን ርዕስ ገፅ)።

ላማናውያን የአይሁድ ቅሪት ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፲፱፡፳፯፡ ጌታ ከመምጣቱ በፊት፣ ላማናውያንም እንደ ፅጌ ረዳ ያብባሉ፣ ት. እና ቃ. ፶፱፡፳፱፡

ላማን፡ *ደግምም ላማናውያን፣ ሌሂ፣ የኔፊ አባት ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ የሌሂና የሳሪያ የመጀመሪያ ልጅ እናም የኔፊ ታላቅ ወንድም (፩ ኔፊ ፪፡፭)። ላማን ጥሩ ከማድረግ በብዙ ጊዜ መጥፎዎችን ለማድረግ መረጠ።

ላማን በአባቱ ላይ አጉረመረመ፣ **፤ ኔፊ** ፪፡፲፩–፲፪። በጻድቅ ወንድሙ በኔፊ ላይ አመጸ፣ **፤ ኔፊ** ፯፡፮ (፩ ኔፊ ፣ ፳፡፳–፳፱)። በሌሂ ራዕይ ውስጥ ከህይወት ዛፍ ፍሬ አልበላም፣ **፤ ኔፊ** ፰፡፴፣–፴፮። እርግማን በላማንና በእርሱ ተከታዮች ላይ መጣ፣ **፪ ኔፊ** ፭፡፳፩ (አልማ ፣ ፯)።

ላሞኒ፡ *ደግምም አሞን፣ የሞዛያ ወንድ ልጅ ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ በጌታ መንፈስና በአሞን የተነሳሱ አገልግሎቶችና ትምህርቶች ምክንያት የተቀየረው የላማናውያን ንጉስ (አልማ ፲፯–፲፱)።

ላባን፣ የርብቃ ወንድም። *ደግሞም ርብቃ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የርብቃ ወንድም እና የያዕቆብ ባለቤቶች የልያ እና የራሔል አባት (ዘፍጥ. ᏕᏬ፡ᏕᏬᏥ–ᏕᏣ፣ ᏕᏦ፡ᏯᏢ–ᏯᏬ፣ ᏕᏕᏣ፡ᏔᏩ–ᏕᏣ፣ ᏕᏥ፡ᏬᏬ–ᏯᏥ፣ ᏯᏩ፡ᏕᏕᏣ–ᏯᏦᏩ)።

ላባን፣ የነህስ ሰሌዳዎች ጠባቂ። *ደግሞም የነህስ ሰሌዳዎች ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ በሌሂ ቤተሰብ ዘመን ውስጥ በኢየሩሳሌም የነህስ ሰሌዳዎችን የሚጠብቅ ሰው። ላባን ኔፊንና ወንድሞቹን ዘረፋቸው እናም ሊገድላቸው ሞከረ (Ꮣ ኔፊ Ᏸ፡Ꮣ–ᏕᏦ)። ሰሌዳዎችን ለማግኘት ኔፊ ላባንን እንዲገድል በመንፈስ ተገፋፋ (Ꮣ ኔፊ Ᏽ፡Ꮣ–ᏕᏦ)።

ሌሂ፣ የኔፊ አባት

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ ቤተሰቡን እና ተከታዮቹን ከኢየሩሳሌም በምእራብ ክፍለ አለም ውስጥ ወደሚገኘው ወደ ቃል ኪዳን ምድር የመራ የእብራውያን ነቢይ። በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ ሌሂ በህዝቦቹ መካከል የነበረ የመጀመሪያ ነቢይ ነበር።

ሌሂ ከቤተሰቡ ጋር ከኢየሩሳሌም የሸሸው በጌታ ትእዛዝ መሰረት ነበር (Ꮣ ኔፊ Ᏼ፡Ꮣ–Ᏽ)። እርሱም በግብፅ ይተሸጠው ዮሴፍ ትውልድ ነበር (Ꮣ ኔፊ Ꮥ፡Ꮵᏽ)። ጌታ ስለህይወት ዛፍ ራዕይ ሰጠው (Ꮣ ኔፊ ᏕᏬ፡Ᏼ–ᏯᏕ)። ሌሂና ወንድ ልጆቹ መርከብ ሰሩ እናም ወደ ምዕራብ ክፍለ አገር ተጓዙ (Ꮣ ኔፊ ᏥᏦ–ᏥᏕᏬ)። እርሱና ትውልዶቹ በአዲሱ ምድር ተመሰረቱ (Ꮣ ኔፊ ᏥᏕᏬ፡ᏕᏥ–ᏕᏕᏕ)። ከመሞቱ በፊት፣ ሌሂ ልጆቹን ባረከ እናም ስለክርስቶስና በጓሊኛው ቀናት መፅሐፈ ሞርሞን ስለመምጣቱ አስተማራቸው (Ᏼ ኔፊ Ꮥ፡Ꮣ–Ᏽ፡Ꮵᏼ)።

መፅሐፈ ሌሂ፣ ጆሴፍ ስሚዝ መፅሐፈ ሞርሞንን ሲተረጉም በመፅሐፈ ሌሂ ነበር የጀመረው። ይህም ሞርሞን ከሌሂ ሰሌዳ አሳጥሮ የጻፈው መዝገብ ነበር። ከመፅሐፉ የተረጎማቸውን ᏧᏥᏬ ገጾች ከነበረው በኋላ፣ ጆሴፍ፣ በመፅሀፈ ሞርሞን መተርጎም ጊዜ ለጆሴፍ እንደ ጸሀፊ ላገለገለው፣ ለማርቲን ሀርስ ያልታተመ መፅሐፍን ሰጠ። ገጾቹ ጠፉ። ጆሴፍ የጠፋውን ያልታተመ መፅሐፍ ለመተካት መፅሐፈ ሌሂን እንደገና አልተረጎመም፣ ነገር ግን በዚህ ምትክ ከዚህ ጋር የተገናኙ ታሪኮችን ከወርቅ ሰሌዳዎች ተረጎመ (ት. እና ቃ. Ᏸ፡ Ꮵ መግቢያዎችን ተመልከቱ)። እነዚህ ታሪኮች አሁን የመፅሐፈ ሞርሞን የመጀመሪያው ስድስት መፅሐፎች ናቸው።

ሌሂ፣ የኔፋውያን ሚስዮን። *ደግሞም ሔለማን፣ የሔለማን ልጅ ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ የሔለማን ልጅ የነበረው የሔለማን ልጅ። ሌሂ ታላቅ ሚስዮን ነበር (ሔለ. Ᏸ፡ᏕᏥ፣ Ᏼ፡Ꮵᏼ)።

የሌሂ ስም የተሰጠው ስለቅድመ አያቱ እንዲያስታውስ ነው፣ ሔለ. Ꮥ፡Ᏼ–Ᏽ። ከኔፊ ጋር ብዙ ተቀያሪዎች አገኘ፣ ታሰረ፣ በእሳት ተከበበ፣ እናም ከመላእክት ጋር ተነጋገረ፣ ሔለ. Ꮥ፡Ꮵᏼ–ᏯᏕ። በየቀኑ ብዙ ራዕዮችን ተቀበሉ፣ ሔለ. ᏥᏬ፡ᏕᏥ።

ሌሂ፣ የኔፋውያን የወታደሮች አዛዥ

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ የኔፋውያን የወታደሮች አዛዥ (አልማ ᏯᏥ፡ᏭᏕ–ᏯᏥ፣ ᏯᏩ፡ᏥᏦ–ᏥᏦ፣ ᏯᏫ፡ᏕᏦ–ᏭᏦ፣ ᏯᏥ፡ᏫᏬ፣ ᏕᏬ፡ᏥᏕ–ᏕᏬ)።

ሌዊ። *ደግሞም እስራኤል፣ ያዕቆብ፣ የይስሐቅ ልጅ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የያዕቆብ እና የልያ ሶስተኛ ወንድ ልጅ (ዘፍጥ. ᏕᏩ፡ᏭᏬ፣ ᏭᏬ፡ᏕᏥ)። ሌዊ ከእስራኤል ጎሳዎች አንዱ አባት ሆነ።

የሌዊ ጎሳ፣ ያዕቆብ ሌዊንና ትውልዶቹን ባረከ (ዘፍጥ. ᏯᏩ፡Ᏼ–Ꮣ፣ ᏕᏣ)። የሌዊ ትውልዶች በእስራኤል ቅድስተ ቅዱሳን ቦታዎች አገለገሉ (ዘኁል. Ᏼ፡ᏯᏦ–ᏯᏬ)። አሮን ሌዊ ነበር፣ እናም የእርሱ ትውልዶች ካህናት ነበሩ (ዘፀአ. Ᏽ፡ᏥᏦ–ᏕᏣ፣ ᏕᏣ፡Ᏼ–ᏬᏥ፣ ᏕᏩ)። ሌዋውያን የአሮን ወንድ ልጆች የሆኑ ካህናትን ይረዱ ነበር (ዘኁል. Ᏸ፡Ᏼ–Ꮵ፣ Ᏼ ነገሥ. ᏣᏥ፡Ᏼ)። አንዳንዴም እንደ ዘማሪዎች (Ᏼ ዜና ᏥᏕ፡ᏥᏦ፣ ነህ. ᏥᏕ፡ᏕᏪ)፣ ለመስዋዕት የመጡትን የሚያርዱ (Ꮺ ዜና ᏕᏩ፡ᏭᏬ፣ ዕዝ. Ᏽ፡ᏕᏥ)፣ እና በአጠቃላይም በቤተመቅደስ ውስጥ የሚረዱ (ነህ. ᏥᏕ፡ᏥᏦ) ነበሩ። ሌዋውያን ስርዓቶችን ለእስራኤል ልጆች በማከናወን ጌታን ለማገልገል የተቀደሱ ነበሩ። ሌዋውያን እራሳቸውም ለእስራኤል ልጆች ጥቅም በመስዋዕት የቀረቡም ነበሩ (ዘኁል. ᏣᏥ፡ᏥᏕ–ᏕᏪ)፣ በዚህም በበኩራት ምትክ ለእርሱ የተሰጡ የእግዚአብሔር ልዩ ንብረቶች ሆኑ (ዘኁል. ᏣᏥ፡ᏥᏦ)። የተቀደሱ አልነበሩም፣ ነገር ግን ለሀላፊነታቸው የጸዱ ነበሩ (ዘኁል. ᏣᏥ፡Ᏽ–ᏥᏦ)። በከነዓን ውርስ ነበራቸው (ዘኁል. ᏥᏣ፡ᏕᏥ–ᏕᏪ) አስራትን (ዘኁል. ᏥᏣ፡ᏕᏕ)፣ አርባ ስምንት ከተማዎችን (ዘኁል. ᏭᏕ፡Ᏽ)፣ እና በበአል ጊዜ የህዝቦችን ምዕዋት ለመቀበል መብትን (ዘዳግ. ᏥᏪ፡ᏥᏣ–ᏥᏩ፣ ᏥᏬ፡ᏕᏦ–ᏕᏩ) ተቀበሉ።

ልሙኤል። *ደግሞም ላማናውያን፣ ላማን፣ ሌሂ፣ የኔፊ አባት ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ የሌሂ ሁለተኛ ወንድ ልጅ እና ከኔፊ ታላቅ ወንድሞች አንዱ። ኔፊን ለመቃወም ከወንድሙ ጋር አንድ ሆነ።

ሌሂ ልሙኤልን እንደሸለቆ የማይነቃነቅ እንዲት ሆን ገሰጸው፣ Ᏼ ኔፊ Ᏽ፡Ꮵ። ኔፊ ላይ ተናደደ፣ የላማ

ንን ቃላት አድምጦአል፣ ፤ ኔፊ ፲፰፡፳፯። ልሙኤላ ውያን ከላማናውያን ጋር ተጨምረው ነበር፣ *ያዕቆ.* ፤፡፲፮–፲፱ (አልማ ፵፯፡፴፭)።

ልሳን። ምላስ *ተመልከቱ*

ልበ ሙሉነት። *ደግሞም መታመን፤ እምነት፣ ማመን ተመልከቱ*

በአንድ ነገር ላይ፣ በልዩም በአግዚአብሔእር ወይም በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ፣ ማረጋገጫ፣ ማመን፣ ወይም እምነት መጣል።

በሰው ከመታመን ይልቅ በእግዚአብሔር መታመን ይሻላል፣ መዝ. ፻፲፰፡፰። እግዚአብሔር መታመኛህ ይሆናልና፣ ምሳ. ፫፡፳፮።

ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ፣ እምነት ይሆንልናል፣ ፤ ዮሐ. ፪፡፳፰።

ክፉ ኔፋውያን የልጆቻቸውን መተማመን አጡ፣ *ያዕቆ.* ፪፡፴፭።

ያሳምር፤ ከዚያም ልበ ሙሉነትህ በእግዚአብሔር ፊት እየጠነከረ ይሄዳል፣ ት. እና ቃ. ፲፳፭፡፴፭።

ልብ። *ደግሞም የተሰበረ ልብ፤ ዳግመኛ መወለድን፣ ከእግዚአብሔር መወለድ ተመልከቱ*

የሰው አዕምሮና ፍላጎት ምሳሌ እናም የስሜቶች ሁሉ ምሳሌአዊ ምንጭ።

አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ ውደድ፣ ዘዳግ. ፮፡፭ (ዘዳግ. ፮፡፲–፮፣ ማቴ. ፳፪፡፴፯፣ ሉቃ. ፲፡፳፯፣ ት. እና ቃ. ፹፱፡፭)። እግዚአብሔር እንደ ልቡ የሆነ ሰው መርጦአል፣ ፤ ሳሙ. ፲፫፡፲፬። ሰው ፊትን ያያል፣ እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል፣ ፤ ሳሙ. ፲፮፡፯። እጆቹ የነጹ፥ ልቡም ንጹሕ የሆነ፥ ወደ እግዚአብሔር ተራራ ይወጣል እናም ይባረካል፣ መዝ. ፳፬፡፫–፭ (፪ ኔፊ ፳፭፡፲፮)። በልቡ እንዳሰበ እንዲሁ ነውና፣ ምሳ. ፳፫፡፯። ኤልያስ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች፥ የልጆችንም ልብ ወደ አባቶች ይመልሳል፣ ሚል. ፬፡፭–፮ (ሉቃ. ፩፡፲፯፣ ት. እና ቃ. ፪፡፪፣ ፻፲፡፲፬–፲፭፣ ፻፴፳፡፴፯፣ ፵፯፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፴፳–፴፱)።

ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው፣ ማቴ. ፭፡፰ (፫ ኔፊ ፲፪፡፰)። ሰው ከልብ መልካም ወይም ከልብ ክፉ መዝገብ ይናገራል፣ ሉቃ. ፮፡፵፭።

በሙሉ ልባችሁ አላማ ወልድን ተከተሉ፣ ፪ ኔፊ ፴፩፡፲፫። በመንፈስ ከእግዚአብሔር የተወለዳችሁ ናችሁን? በልባችሁስ ይህን ታላቅ ለውጥ ተለማምዳ ችኋልን፣ አልማ ፭፡፲፬። ለጌታ መስዋእት የተሰበረ ልብ እናም የተዋረደ መንፈስ ታቀርባላችሁ፣ ፫ ኔፊ ፱፡፳ (፫ ኔፊ ፲፪፡፲፱፣ ኤተር ፬፡፲፭፣ ሞሮኒ ፮፡፪)።

በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በአዕምሮህ እና በልብህ እነግርሃለሁ፣ ት. እና ቃ. ፰፡፪።

ልያ። *ደግሞም ላባን፣ የርብቃ ወንድም፤ ያዕቆብ፣ የይስሐቅ ልጅ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የላባን የመጀመሪያ ሴት ልጅ እና ከያዕቆብ ባለቤቶች አንዷ (ዘፍጥ. ፳፱)። ልያ የ ስድስት ወንድ ልጆች እና የአንድ ሴት ልጅ እናት ሆነች (ዘፍጥ. ፳፱፡፴–፴፭፣ ፴፡፲፯–፳፩)።

ልጅ፣ ልጆች። *ደግሞም መልስ መስጠት፣ ሂሳብ፣ ተጠያቂነት፣ ሀላፊነት፤ መባረክ፣ የተባረከ፣ በረከት—ልጆችን መባረክ፣ ቤተሰብ፤ የህጻን ጥምቀት፤ የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ፤ ደህንነት—የልጆች ደህንነት ተመልከቱ*

ወጣት ሰው፣ ጉልምስና ላይ ገና ያልደረሰ። አባቶች እና እናቶች ልጆቻቸውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዲያከብሩ ያሰልጥኑአቸው። ልጆች የአቅመ አዳም እድሜ ላይ እስከሚደርሱ ድረስ ኃጢያት የላቸውም (ሞሮኒ ፰፡፳፪፤ ት. እና ቃ. ፹፹፡፳፤)።

ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው፣ መዝ. ፻፳፯፡፫–፭። ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው፣ ምሳ. ፳፪፡፮። ሕፃናትን ተዉአቸው፣ ወደ እኔም ይመጡ ዘንድ አትከልክሉአቸው፣ ማቴ. ፲፱፡፲፬። ለወላጆቻችሁ ታዘዙ፣ ኤፌ. ፮፡፩–፫ (ቁላ. ፫፡፳)።

ያለውድቀት፣ አዳም እና ሔዋን ልጆች አይኖሯቸውም ነበር፣ ፪ ኔፊ ፪፡፳፪–፳፫። በእውነትና በጥሞና መንገድ እንዲራመዱ ልጆችን አስተምሯቸው፣ ሞዛያ ፬፡፲፬–፲፭። ትንንሽ ልጆች ዘለዓለማዊ ህይወት ይኖራቸዋል፣ ሞዛያ ፲፭፡፳፭። ኢየሱስ ህፃናቶቻቸውን ወሰዳቸውና ባረካቸውም፣ ፫ ኔፊ ፲፯፡፳፩። እናም ልጆችሽ ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ፤ እናም የልጆችሽም ሰላም ታላቅ ይሆናል፣ ፫ ኔፊ ፳፪፡፲፫ (ኢሳ. ፶፬፡፲፫)። ህጻናት ንስሀ መግባት እና መጠመቅ አያስፈልጋቸውም፣ ሞሮኒ ፰፡፰–፳፬።

ህጻናት ከአለም መጀመሪያ ጀምሮ በአንድያ ልጁ ድነዋል፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፴፯–፴፱። ወላጆች ልጆቻቸውን የወንጌል መሰረታዊ መርሆችን እና ስራዎችን ማስተማር ይገባቸዋል፣ ት. እና ቃ. ፹፹፡፳፭፣ ፳፯–፳፰። ትንንሽ ልጆች በክርስቶስ ኃጢያት ክፍያ በኩል የተቀደሱ ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፫፬፡፭፡፮። ወላጆች ልጆቻቸውን በብርሀን እና በእውነት እንዲያሳድጓቸው ታዝዘዋል፣ ት. እና ቃ. ፶፫፡፴። በተጠያቂነት እድሜዎች ከመድረሳቸው በፊት የሞቱት ልጆች በሰለስቲያል መንግስት ውስጥ ድነዋል፣ ት. እና ቃ. ፲፴፯፡፲።

ልግስና። *ደግሞም ርህራሄ፤ በጎ ድርጊት፤ አገልግሎት፤ ፍቅር ተመልከቱ*

የክርስቶስ ንጹህ ፍቅር (ሞሮኒ ፯፡፵፯)፤ ክር

ስቶስ ለሰው ልጆች ያለው እና የሰው ልጆች እርስ በራስ ሊኖራቸው የሚገባቸው ፍቅር (፪ ኔፊ ፳፯፡፡ ፴፣ ፴፫፡፡ ፲፡ ኤተር ፲፪፡ ፴፫–፴፭)፤ መው ደድ ብቻ ሳይሆን፣ ከሁሉም በላይ፣ ልዑላዊ፣ ጠን ካራ አይነት የሆነ ፍቅር።

እውቀት ያስታብያል ፍቅር ግን ያንጻል፣ ፩ ቆሮ. ፰፡ ፩። ንጹ ፍቅር የሆነው ልግስና ከሁሉም በላይ ምርጥ እና የበለጠ ነው፣ ፩ ቆሮ. ፲፫። የትእዛዝ ፍጻሜ ግን ከንጹሕ ልብ የሚወጣ ፍቅር ነው፣ ፩ ጢሞ. ፩፡ ፭። በወንድማማችም መዋደድ ፍቅ ርን ጨምሩ፣ ፪ ጴጥ. ፩፡ ፯።

ጌታ ሰው ሁሉ ለጋስ መሆን እንዳለበት ትዕዛ ዝን ሰጥቷል፣ ፪ ኔፊ ፳፯፡ ፴ (ሞሮኒ ፯፡ ፴፱–፴፯)። እምነት፣ ተስፋ፣ እና ልግስና ይኑራችሁ፣ አልማ ፯፡ ፳፱። ጌታ ለሰዎች ያለው ፍቅር ልግስና ነው፣ ኤተር ፲፪፡ ፴፫–፴፱። ሰዎች ልግስና ከሌላቸው በአ ባትህ መኖሪያ ያዘጋጀኸውን ስፍራ ሊወርሱ አይች ሉም፣ ኤተር ፲፪፡ ፴፱ (ሞሮኒ ፲፡ ፳–፳፩)። ሞሮኒ የሞርሞን እምነት፣ ተስፋ፣ እና ልግስና ቃላትን ጻፈ፣ ሞሮኒ ፯።

ልግስና ሰዎችን ለጌታ ስራ ብቁ ያደርጋቸዋል፣ ት. እና ቃ. ፱፡ ፭–፮ (ት. እና ቃ. ፲፪፡ ፳)። በል ግስና ማሰሪያ ራሳችሁን አልብሱ፣ ት. እና ቃ. ፹፯፡ ፻፳፭። በልግስና ማሰሪያ ራሳችሁን አል ብሱ፣ ት. እና ቃ. ፻፳፭፡ ፻፷፭።

ሎጥ። ደግሞም አብርሐም ተመልከቱ

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የሐራን ልጅ እና የአብር ሐም የወንድም ልጅ (ዘፍጥ. ፲፩፡ ፳፯፣ ፴፩፣ አብር. ፪፡ ፱)። ሐራን በዑር ውስጥ በርሀብ ምክንያት ሞተ (አብር. ፪፡ ፩)። ሎጥ ከዑር ከአብርሐም እና ከሳራ ጋር ወጣ እናም ከእነርሱ ጋር ወደከነዓን ተጓዘ (ዘፍጥ. ፲፪፡ ፱–፭)። ሎጥ በሰዶም ለመኖር መረጠ። በህዝቡ ክፉነት ምክንያት ጌታ ሰዶምን ከማጥፋቱ በፊት ሎጥ እንዲሸሽ እንዲያስጠነቅቁት ጌታ መልእክተ ኞች ላከ (ዘፍጥ. ፲፱፡ ፳–፲፫፣ ፲፱፡ ፩፣ ፲፫፣ ፲፭)፤ ነገር ግን፣ የሎጥ ባለቤት ድምሰሳውን ለመመል ከት ወደኋላ ተመለከተች እናም የጨው ሐውልት ሆነች (ዘፍጥ. ፲፱፡ ፳፮)። አዲስ ኪዳን ስለሎጥ ይጠ ቅሳሉ (ሉቃ. ፲፯፡ ፳፱፣ ፪ ጴጥ. ፪፡ ፮–፯)። ከአብር ሐም ከተለያየ በኋላ ስለነበረው ህይወቱ በዘፍጥረት ፲፫፣ ፲፰፡ እና ፲፱ ተገልጸዋል።

ሐሜት። ክፉ መናገር ተመልከቱ

ሐሰት። ደግሞም ሽንገላ (ውሸት)፣ መዋሸት፣ ማታለል፣ ታማኝ፣ ታማኝነት፣ ክፉ መናገር ተመልከቱ

ለማታለል የሚደረግ ምንም አይነት የውሸት ንግ ግር።

አትስረቁ፥ አትካዱም፥ ከእናንተም እርስ በር ሳችሁ ሐሰት አትነጋገሩ፣ ዘሌዋ. ፲፱፡ ፲፩። ዓመፃን ጠላሁ ተጸየፍሁም፣ መዝ. ፻፲፱፡ ፻፷፫። ውሸተኛ ከንፈር በእግዚአብሔር ዘንድ አሰጸያፊ ነው፣ ምሳ. ፲፪፡ ፳፪። ሕዝቤ ሐሰትን የማያደርጉ ልጆች ናቸው፣ ኢሳ. ፷፫፡ ፰።

ዲያብሎስ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነው፣ ዮሐ. ፰፡ ፵፬ (፪ ኔፊ ፪፡ ፲፰፣ ኤተር ፰፡ ፳፭፣ ሙሴ ፬፡ ፬)። እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አልዋሸህም፣ የሐዋ. ፭፡ ፬ (አልማ ፲፪፡ ፫)። ማንም እግዚአብ ሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው፣ ፩ ዮሐ. ፬፡ ፳። ሐሰተኛዎች ሁሉ በሁለተኛው ሞት ክፍል አላቸው፣ ራዕ. ፳፩፡ ፰ (ት. እና ቃ. ፰፫፡ ፲፯)።

ለውሸታም ወዮለት፣ ወደታች ወደ ሲያል ይጣ ላልና፣ ፪ ኔፊ ፱፡ ፴፬። ትንሽም ዋሹ በዚህ ምንም ጉዳት የለም በማለት ብዙዎች ያስተምራሉ፣ ፪ ኔፊ ፳፰፡ ፰–፱ (ት. እና ቃ. ፣ ፡ ፳፭)። ለጌታ መዋሸት እንችላለን ብላችሁ ትገምታላችሁ፣ አልማ ፭፡ ፲፯። አንተ የእውነት አምላክ ነህና፣ ለመዋሸት አትች ልም፣ ኤተር ፫፡ ፲፪ (ዘኍል. ፳፫፡ ፲፱፣ ፩ ሳሙ. ፲፭፡ ፳፱፣ ቲቶ ፩፡ ፪፣ ዕብ. ፮፡ ፲፰፣ ኢሳ ፩፡ ፮)።

ሃሰት የሚናገር እናም ንሰሃ የማይገባ ወደ ውጭ ይጣላል፣ ት. እና ቃ. ፵፪፡ ፳፩። ውሸታሞቹ የቲለ ስቲያል ክብርን ይወርሳሉ፣ ት. እና ቃ. ፫፯፡ ፻፫–፻፮።

በታማኝነት እናምናለን፣ እ.አ. ፩፡ ፲፫።

ሐና፣ ሊቀ ካህኑ። ደግሞም ቀያፋ ተመልከቱ

በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ በሳንሀድርን ውስጥ ታላቅ ተፅዕኖ ያለው ሰው። ኢየሱስ መጀመሪያ ሲያዝ ወደ እርሱ ተወስዶ ነበር (ዮሐ. ፲፰፡ ፲፫)፤ ሐዋሪያት ለፍርድ በቀረቡበት ጊዜም የመሪ ሀላፊነትም ነበ ረው (የሐዋ. ፬፡ ፮–፯)።

ሐና፣ የሳሙኤል እናት። ደግሞም ሳሙኤል፣ የብሉይ ኪዳን ነቢይ ተመልከቱ

የብሉይ ኪዳን ነቢይ ሳሙኤል እናት። ጌታ ሳሙ ኤልን ለሐና እንደ ጸሎቷ መልስ ሰጣት (፩ ሳሙ. ፩፡ ፲፩፣ ፳–፳፪)። ሐና ሳሙኤልን ለጌታ ቀደሰች። የምስጋና መስጠት መዝሙሯ ከኢየሱስ እናት ማሪ ያም ጋር የሚነጻጸር ነው (፩ ሳሙ. ፪፡ ፩–፲፣ ሉቃ. ፩፡ ፵፮–፶፭)።

ሐና፣ ነቢይቷ

በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ የአሴር ጎሳ ነቢይቷ። ኢየ ሱስ በተወለደበት ጊዜ፣ እጅግ ያረጀች መበለት ነበ ረች። ሕጻኑ ኢየሱስ በቤተመቅደስ ውስጥ በሚቀረ ብበት ጊዜ አየችው እና እንደ ቤዛ አወቀችው (ሉቃ. ፪፡ ፴፮–፴፰)።

ሐዋሪያ፡ ደግምም ራዕይን፤ ደቀ መዛሙርትን ተመልከቱ

በግሪክ ቋንቋ፣ ሐዋሪያ ማለት “የተላከ” ማለት ነው። ኢየሱስ በምድር አገልግሎቱ ጊዜ የቅርብ ደቀ መዛሙርቱ እና ረጂዎቹ እንዲሆኑ መርጦ ለሾማ ቸው የሰጣቸው ማዕረግ ነበር (ሉቃ. ፮፡፲፫፣ ዮሐ. ፲፭፡፲፮)። ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ እርሱን እንዲወ ክሉ እና በእርሱ በኩል እንዲያገለግሉ ላካቸው። በጥንት እና ዛሬ ዳግማ በተመለሰችው ቤተክርስ ትያን አስራ ሁለት ሐዋሪያት ቡድን ውስጥ፣ ሐዋ ሪያ በአለም ውስጥ ሁሉ ስለእርሱ መለኮታዊነት እና ከሞት ስለመነሳቱ ለመመስከር ልዩ የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክሮች የሆኑ ናቸው (የሐዋ. ፩፡፳፪፤ ት. እና ቃ. ፲፯፡፳፫)።

የክርስቶስ ቤተክርስትያን በሐዋሪያት እና ነቢ ያት መሰረት ላይ ታንጻለች፣ ኤፌ. ፪፡፳፣ ፬፡፲፩። ሌሒና ኔፊ አስራ ሁለቱ ሐዋሪያት ኢየሱስን ሲከ ተሉ ተመለከቱ፣ ፩ ኔፊ ፩፡፲፣ ፲፩፡፴፬። ሐዋሪ ያት የእስራኤል ቤት ላይ ይፈርዳሉ፣ ሞር. ፫፡፲፯።

የነቢያትንና የሐዋሪያትን ቃላት የማያዳምጡ ይገለላሉ፣ ት. እና ቃ. ፩፡፲፬ (፫ ኔፊ ፲፪፡፩)። የአስራ ሁለቱ ጥሪና ተልዕኮ ተገልጸው ነበር፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፳፯–፴፯። ጆሴፍ ስሚዝ እንደ ሐዋ ሪያ ተሾመ፣ ት. እና ቃ. ፳፡፪፣ ፳፩፡፩። ሐዋሪያት የክርስቶስ ስም ልዩ ምስክሮች ናቸው እናም የአገ ልግሎትን ቁልፎች ይዘዋል፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፲፪ (ት. እና ቃ. ፲፲፪፡፴–፴፪)። አስራ ሁለቱ ሐዋሪ ያት ከቀዳሚ አመራር ጋር እኩል ስልጣን እና ሀይል ያለው ቡድን ይሰራሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፳፫–፳፬። አስራ ሁለቱ የሚጓዙ ከፍተኛ ሸንጎዎች ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፴፫። ሐዋሪያት የሚስዮን ስራ ቁል ፎችን ይዘዋል፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፴፭። የሐዋሪያት አንዳንድ ሀላፊነቶች ተዘርዝረዋል፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፶፪። ለአስራ ሁለቱ በሙሉ እላለሁ፡ ተከተ ለኝ፣ እና በጎቼን መግብ፣ ት. እና ቃ. ፲፲፪፡፲፬–፲፭።

በሐዋሪያት እናምናለን፣ እ.አ. ፩፡፯።

የሐዋሪያት መመረጥ፣ ሐዋሪያት በጌታ የተመ ረጡ ናቸው (ዮሐ. ፮፡፫፣ ፲፭፡፲፮)።

ከደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ አስራ ሁለት ሐዋሪያት መረጠ፣ ሉቃ. ፮፡፲፫–፲፮። ማትያስ እንደ ሐዋሪያ ተመረጠ፣ የሐዋ. ፩፡፳፭–፳፮።

ኦሊቨር ካውደሪና ዴቪድ ዊትመር አስራ ሁለትን እንዲፈልጉ ትእዛዝ ተሰጥቷቸው ነበር፣ ት. እና ቃ. ፲፳፡፴–፴፪።

ሐጋዝ

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ መርከብ የሚገነባ ኔፋ ውያን (አልማ ፳፫፡፭–፯)።

ሐጌ

በ፭፻፳ ም.ዓ. አካባቢ፣ የአይሁዳ ህዝብ ከባቢሎን ውስጥ ከስደት ወዲያው እንደተመለሱ በኢየሩሳሌም ውስጥ የተነበየ ነቢይ (ዕዝ. ፭፡፩፣ ፮፡፲፬)። የጌታን ቤተመቅደስ በኢየሩሳሌም ውስጥ እንደገና ስለመገ ንባት ተናገረ እናም ስላልተፈጸመም ህዝብን ገሰጸ። ደግሞም ስለአንድ ሺህ አመቱ ቤተመቅደስ እና ስለ ጌታ ዘመነ መንግስት ጻፈ።

ትንቢተ ሐጌ፣ በምዕራፍ ፩ ውስጥ፣ ጌታ ህዝብን ቤተመቅደሱ ገና ሳይገነባ እነርሱ ተገንብቶ በተፈ ጸመ ቤታቸው ውስጥ ስለሚኖሩ ገሰጻቸው። ምዕ ራፍ ፪ ጌታ በቤተመቅደሱ ውስጥ ሰላም እንደሚ ሰጥ ሐጌ የተነበየውን ይመዘግባል።

ሒምኒ፡ ደግምም ሞዛያ፣ የቢንያም ልጅ፤ የሞዛያ ልጆች ተመልከቱ

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ የንጉስ ሞስያ ወንድ ልጅ። ሒምኒ ከወንድሞቹ ጋር ለላማናውያን ለመስ በክ ሄደ (ሞዛያ ፳፯፡፲–፲፩፣ ፴፱–፴፯፣ ፳፰፡፩–፱)።

ሔለማን፣ የሔለማን ልጅ

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ የኔፋውያንን ህዝቦች ያስተማረው ነቢይ እና መዝገብ ጠባቂ። እርሱም የታናሹ አልማ የልጅ ልጅ እና በሁሉም ነገሮች ላይ ሀይል የተሰጠው ኔፊ አባት ነበር። ከልጁ ኔፊ ጋር፣ ሔለማን መፅሐፈ ሔለማንን ጻፈ።

መፅሐፈ ሔለማን፣ ምዕራፍ ፩–፪ ታላቅ የፖለቲካ ችግርን ይገልጻሉ። ምዕራፍ ፫–፬ ሔለማን እና የኔ ፋውያን ሰራዊት ዋና ሻምበል የሆነው ሞሮኒህ በመ ጨረሻም ለጊዜ ሰላም ለመመስረት ቻሉ። ነገር ግን፣ እነዚህ ጥሩ ሰዎች የእነርሱ መሪዎች ቢሆኑም፣ ህዝ ቦቹ በክፋት ጨመሩ። በሔለማን ፭፡፩–፮፡፲፬ ውስጥ ኔፊ አያቱ አልማ እንዳደረገው ህዝቡን ለማስተማር የፍርድ ወንበሩን ተወ። ለጊዜው ህዝቡ ንስሀ ገባ። በሔለማን ፮፡፲፭–፲፱፡፳፯ ውስጥ ግን የኔፋውያን ህዝብ ክፉ ሆኑ። በመጨረሻው ምዕራፍ ፲፫–፲፮ ስለ አዳኝ መወለድ እና መሰቀል እና እነዚህን ድርጊ ቶች ስለሚያሳዩት ምልክቶች አስቀድሞ ስለተና ገረ ላማናውያን ሳሙኤል ስለተባለው ነቢይ አስደ ናቂ ታሪክን ይዘዋል።

ሔለማን፣ የንጉስ ቢንያም ልጅ፡ ደግምም ቢንያም፣ የሞዛያ አባት ተመልከቱ

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ ከንጉስ ቢንያም ሶስት ወንድ ልጆች አንዱ (ሞዛያ ፩፡፪–፳)።

ሔለማን፣ የአልማ ልጅ፡ ደግምም አልማ፣ የአልማ ወንድ ልጅ፤ አንቲ-ኔፊ-ሌሂ፤ የሔለማን ልጆች ተመልከቱ

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ የአልማ ልጅ አልማ

ታላቅ ልጅ (አልማ ፴፭፡፲፯)። ሔለማን ነቢይ እና የጦር ሀይል መሪ ነበር።

አልማ የህዝቡን መዝገቦች እና የያሬዳውያን ሰሌዳዎችን ለልጁ ለሔለማን ሰጠ፣ **አልማ** ፴፯፡፩–፪፣ ፳፩። አልማ ሔለማንን የህዝቡን ታሪክ በመጻፍ እንዲቀጥል አዘዘው፣ **አልማ** ፴፭–፴፪። ሔለማን ቤተ ክርስቲያኗን እንደገና መሰረተ፣ **አልማ** ፴፭፡፳፪–፳፫። ሁለት ሺህ አሞናውያን ጀግናዎች ሔለማን መሪአቸው እንዲሆን ፈለጉት፣ **አልማ** ፴፫፡፲፱፣ ፳፪። ሔለማን እና ብላቴና አሞናውያን ከላማና ውያን ጋር ተዋጉ እናም በእምነትም ዳኑ፣ **አልማ** ፴፯፡፲፱–፳፯።

ሔኖክ። *ደግሞም ፅዮን ተመልከቱ*

የፅዮን ከተማ ህዝቦችን የመራ ነቢይ። አገልግሎቱ በብሉይ ኪዳን እና በየታላቅ ዋጋ ዕንቁ ውስጥ ተወያይተዋል። ከአዳም በኋላ ሰባተኛው የአባቶችም አለቃ ነበር። የያሬድ አባት እና የማቱሳላ አባት ነበር (ዘፍጥ. ፭፡፲፰–፳፬፣ ሉቃ. ፫፡፴፯)።

ሔኖክ ታላቅ ሰው ነበር እና የመፅሐፍ ቅዱስ አጭር ታሪክ ከሚገልጸው በላይ ታላቅ የሆነ አገ ልግሎት ነበረው። መፅሐፍ ቅዱስ እንደተቀየረ ይጠቅሳል (ዕብ. ፲፩፡፭) ነገር ግን ስለአገልግሎቱ ምንም መግለጫ አይሰጥም። ይሁዳ ፩፡፲፬ የተነበየ ውን ይጠቅሳል። የኋለኛው ቀን ራዕይ ስለሔኖክ፣ በልዩም ስለስበካው፣ ፅዮን ተብላ ስለተጠራችው ከተማው፣ ስለራዕዩ፣ እና ስለትንቢቶቹ በተጨማሪ ይገልጻል (ት. እና ቃ. ፲፯፡፴–፴፯፣ ሙሴ ፮–፯)። ፅዮን በእዚያ በሚኖሩት ጽድቅ ምክንያት ወደሰማይ ተወስዳለች (ሙሴ ፯፡፳–፳፱)።

እግዚአብሔር እራሱን ለሔኖክ ገለጸ፣ **ሙሴ** ፮፡፳፮–፴፯። ሔኖክ ወንጌልን አስተማረ፣ **ሙሴ** ፮፡፴–፳፰። ሔኖክ ህዝቦችን አስተማረ እና ፅዮ ንን መሰረተ፣ **ሙሴ** ፯፡፩–፳፩። ሔኖክ ሁሉንም ነገሮች፣ እንዲሁም የምድርን መጨረሻ አየ፣ **ሙሴ** ፯፡፳፫–፳፰።

ሔዋን። *ደግሞም አዳም፣ ዔድን፣ የአዳም እና የሔዋን ውድቀት ተመልከቱ*

በዚህች ምድር ላይ የኖረች የመጀመሪያዋ ሴት (ዘፍጥ. ፪፡፳፭–፳፭፣ ፫፡፳)። የአዳም ባለቤት ነበረች። በዕብራውያን ቋንቋ የዚህ ስም ትርጉም "ህይወት" ነው። ስሟም የተሰጣት "የሕያዋን ሁሉ እናት" ስለነበረች ነው (ሙሴ ፬፡፳፯)። እርሷ እና የመጀመሪያው ሰው አዳም ለሰው ዘር ዘለአለማዊ እድገት ባደረጉት የዘለአለም ክብርን ይካፈላሉ።

ሔዋን ተፈተነች እናም የተከለከለውን ፍሬ በላች፣ **ዘፍጥ.** ፫ (፪ ኔፊ ፪፡፲፭–፳፣ **ሙሴ** ፬)።

ፕሬዘደንት ጆሴፍ ኤፍ ስሚዝ ሔዋንን በመን ፈስ አለም ውስጥ አየአት፣ **ት. እና ቃ.** ፲፬፡፳፡፴፱። ሔዋን የውድቀት አስፈላጊነት ገባት እናም በቤዛ ነት ተደሰተች፣ **ሙሴ** ፭፡፲፩–፲፪።

ሕመም፣ *ታማሚነት*

በሽታ ወይን ህመም ያለው። በቅዱሣት መጻህ ፍት ውስጥ፣ አንዳንዴ የስጋዊ ህመም የመንፈሳዊ ደህንነት ያለመኖር ምልክት ሆኖ ያገለግላል (ኢሳ. ፩፡፬–፣ ፴፫፡፳፤ ፴፬)።

ጸሎትህን ሰምቻለሁ፡ እንባህንም አይቻለሁ፣ እነሆ፡ እፈውስሃለሁ፣ ፪ ነገሥ. ፳፡፩–፭ (፪ ዜና ፴፪፡፳፤ ፲ሳ. ፴፰፡፩–፭)።

ኢየሱስም በሕዝብም ያለውን ደዌና ሕማም ሁሉ እየፈወሰ ይዞር ነበር፣ **ማቴ.** ፱፡፳፫–፳፱ (፩ ኔፊ ፲፭፡፴፯፣ ሞዛያ ፫፡፭–፣)። ሕመምተኞች እንጂ ባለ ጤናዎች ባለ መድኃኒት አያስፈልጋቸውም፣ **ማቴ.** ፱፡፲–፲፫ (ማር. ፪፡፲፱–፲፯፣ ሉቃ. ፭፡፳፯–፴፪)። ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተ ክርስቲያንን ሽምግሌዎች ወደ እርሱ ይጥራ፣ **ያዕ.** ፭፡፲፱–፲፭።

ክርስቶስ የህዝቡን ህመምና በሽታ በራሱ ላይ ይወስዳል፣ **አልማ** ፯፡፲–፲፪። ኢየሱስ በኔፋ ያን መካከል ሁሉንም በሽተኞንን ፈወሰ፣ ፫ ኔፊ ፳፯፡፲፭።

በደግነት፣ በቅጠላቅጠል እና በለስላሳ ምግብ የታመመውን ይመግብ፣ **ት. እና ቃ.** ፵፪፡፵፫ (አልማ ፵፯፡፵)። በሁሉም ነገሮችም ድህውን የተ ሰቃየውን አስታውሱ፣ **ት. እና ቃ.** ፶፪፡፵። በታ መሙትም ላይ እጆችህን ጫን፣ እናም ይድናሉ፣ **ት. እና ቃ.** ፵፯፡፶።

ሕዝቅኤል

በብሉይ ኪዳን ውስጥ ትንቢተ ሕዝቅኤልን የጻ ፈው ነቢይ። የሳዶቅ ቤተሰብ ካህን እና በናቡከደነፆር በምርኮ ከተወሰዱት አይሁዳ አንዱ ነበር። ከአይሁዳ ተሰዳጆች ጋር በባቢሎን ሰፈረ እናም ለሀያ ሁለት አመት፣ ከ፭፻፺፯ እስከ ፭፻፷ ም.ዓ. ድረስ፣ ተነበየ።

ትንቢተ ሕዝቅኤል፣ የሕዝቅኤል ትንቢት በአ ራት ክፍሎች ለመከፋፈል ይቻላል። ምዕራፍ ፩–፫ ስለ እግዚአብሔር ራዕይና ሕዝቅኤል ለአገልግሎት ስለተጠራበት ይናገራሉ፣ ምዕራፍ ፬–፴፬ በኢየሩሳ ሌም ላይ ስለነበሩ ፍርዶች እና ለምን እንደተሰጡም ይናገራሉ፣ ምዕራፍ ፴፭–፴፱ በሀግሮች ላይ ፍርዶ ችን ያውጃሉ፣ እናም ምዕራፍ ፴፫–፴፰ የኋለኛው ቀን እስራኤል ራዕዮችን ይመዘግባሉ።

ሕዝቅያስ

በብሉይ ኪዳን ውስጥ የይሁዳ ህዝቦች ጻድቅ ንጉስ። ኢሳይያስ የይሁዳ ነቢይ በነበረበት ጊዜ፣ ለሀያ ዘጠኝ አመት ነገሰ (፪ ነገሥ. ፲፰–፳፣ ፪ ዜና ፳፱–፴፪፣ ኢሳ. ፴፯–፴፱)። ኢሳይያስ ቤተክርስ ቲያኗን እና ሀገርን ለማስተካከል ረዳው። ጣዖት

ማምለክ አስቆመ እናም የቤተመቅደስ አገልግሎ ቶችን በድጋሚ መሰረተ። የሕዝቅያስ ህይወት በጸ ሎት እና እምነት ምክንያት ለአስራ አምስት አመት ተራዘመ (፪ ነገሥ. ፳፡፩–፮)። የንግሰ ዘመኑ የመጀ መሪያ ክፍል ሀብታም ነበር፣ ነገር ግን በሶሪያ ንጉስ ላይ ማመጹ (፪ ነገሥ. ፲፰፡፯) ለሁለት ጊዜ በሶ ሪያ እንዲወረር አደረገው፡ የመጀመሪያው በኢሳ ይያስ ፲፡ጽ፬–፴፪ ውስጥ፣ ሁለተኛውም በ፪ ነገስት ፲፰፡፲፫–፲፱፡፯ ውስጥ ተገልጸዋል። ለሁለተኛ ጊዜ በተወረረበት፣ ኢየሩሳሌም በጌታ መልዓክ ዳነች (፪ ነገሥ. ፲፱፡፴፭)።

መሀላ። *ደግሞም ቃል ኪዳን፤ የክህነት መሀላ እና ቃል ኪዳን ተመልከቱ*

በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ እንደሚጠቀሙ በት፣ ቅዱስ ቃል ኪዳን ወይም የተሰፋ ቃል። ነገር ግን፣ ከሰይጣን እና ከመላእክቶቹ በተጨ ማሪ፣ ኃጢያተኛ ሰዎች ክፉ አላማቸውን ለማከና ወን መሀላዎችን ይገባሉ። በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ መሀላዎች ተቀባይ ነበሩ፤ ነገር ግን፣ ሰዎች በእግዚ አብሔር ስም ወይም በእርሱ ፍጥረቶች መሀላ እን ደማይገባቸው ኢየሱስ ክርስቶስ አስተማረ (ማቴ. ፭፡፴፫–፴፯)።

ለአብርሃም የማልሁለትንም መሐላ አጸናለሁ፣ **ዘፍጥ.** ፳፪፡፲። ሰው ነፍሱን በመሐላ ቢያስር፡ ቃሉን አይሰበር፣ **ዘኍል.** ፴፡፪። የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ሁሉ ሥርዓቱን ይጠብቁና ያደርጉ ዘንድ መሐላውን አደረጉ፣ **ነህ.** ፲፡ጽ፱። መሐላዎችህን ለጌታ ስጥ፣ **ማቴ.** ፭፡፴፫ (መክ. ፭፡፬–፭፣ ፲ ኔሬ ፲፪፡፴፫)። እግዚአብሔር ታማ ኞች እንደሚድኑ መሀላ አደረገ፣ **ዕብ.** ፮፡፲፫–፲፰። ዞረም መሃላ ሲገባልን፣ ፍርሃቶች አቆሙ፣ **፩ ኔሬ** ፬፡፴፯። የአሞን ህዝብ በጭራሽ ደም ላለማፍሰስ መሃላን ሰጥተው ነበር፣ **አልማ** ፶፫፡፲፩። ኃጢያተ ኞች ኔፋውያን የሚስጥር መሀላና ቃል ኪዳን ከሰይ ጣን ጋር ገቡ፣ **ሔሊ.** ፮፡ጽ፩–፴። ሰዎች በክህነት ስልጣን መሀላና ቃል ኪዳን የዘ ለአለም ህይወት ያገኛሉ፣ **ት. እና ቃ.** ፸፬፡፴፫–፴፪። በመንፈስ ቅዱስ ቃል ኪዳን ያልታተሙ ቃል ኪዳናት፣ ስምምነቶች፣ የተፈረመበት መረጃዎች፣ ግዴታዎች፣ መሀላዎች፣ ሰዎች ሲሞቱ መጨረሻ አላቸው፣ **ት. እና ቃ.** ፻፴፪፡፲። *መሀሪ፣ ምህረት*። *ደግሞም ኢየሱስ ክርስቶስ፤ የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ፤ ይቅርታ ማድረግ፣ ጸጋ፤ ፍትህ ተመልከቱ*

የርህራሄ፣ የደግነት፣ እና የምህረት መንፈስ። ምህረት ከእግዚአብሔር ጸባያት አንዱ ነው። ኢየ ሱስ ክርስቶስ ለኃጢያት በሚከፍለው መስዋዕቱ በኩል ምህረትን ያቀርብልናል።

እግዚአብሔር መሐሪና ባለ ብዙ ቸርነት ነው፣ **ዘፀአ.** ፴፬፡፮ (ዘዳግ. ፬፡፴፯)። ምህረቱም ለዘላለም ነው፣ **፩ ዜና** ፲፮፡፡ ፴፬፡ ቸርነትህና ምሕረትህ ይከተ ሉኛል፣ **መዝ.** ፳፫፡፮። ለድሀ ግን የሚራራ ምስጉ ነው፣ **ምሳ.** ፲፬፡ጽ፩። ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረ ትን እወድዳለሁ፣ **ሆሴ.** ፮፡፮።

የሚምሩ ብፁዓን ናቸው፡ ይማራሉና፣ **ማቴ.** ፭፡፯ (፲ ኔሬ ፲፪፡፯)። እናንተ ግብዞች አሥራት ስለምታወጡ፡ ፍርድንና ምሕረትን ታማኝነት ንም፡ በሕግ ያለውን ዋና ነገር ስለምትተዉ፡ ወዮ ላችሁ፣ **ማቴ.** ፳፫፡ጽ፫። አባታችሁ ርኅሩኅ እንደ ሆነ ርኅሩኆች ሁኑ፣ **ሉቃ.** ፮፡፴፮። እንደ ምሕረቱ መጠን አዳነን እንጂ፡ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለ ነበረው ሥራ አይደለም፣ **ቲቶ** ፫፡፭።

የጌታ ምህረቶች ርህራሄ በሁሉም ላይ ናቸው፣ **፩ ኔሬ** ፩፡፳። ምህረት ንስህ በማይገባው ሰው ላይ ምንም ሥፍራ አይኖራትም፣ **ሞዛያ** ፪፡፴፯–፴፱። እግዚአብሔር በስሙ ለሚያምኑት ሁሉ መሃሪ ነው፣ **አልማ** ፴፪፡ጽ፪። ምህረት የፍትህን ፍላጎት ሊያሟላ ይችላል፣ **አልማ** ፴፪፡፲፮። ምህረት ፍትህን ይነጥ ቃል ብለህ ትገምታለህ፣ **አልማ** ፵፪፡ጽ፭ (**አልማ** ፵፪፡፲፫–ጽ፭)። ህጻናት በክርስቶስ ምህረት ህያው ሆነዋል፣ **ሞሮኒ** ፯፡፲፱–ጽ (ት. እና ቃ. ፳፱፡፵፯)። የኢየሱስ ክርስቶስ ምህረት ክንድ ለሃጢያታችሁ ክፍያ ሆነ፣ **ት. እና ቃ.** ፳፱፡፩። በስሜ የሚያም ኑት ሁሉ፣ ባፈሰስኩት ደሜ በአብ ፊት አማልጂላ ቸዋለሁ፣ **ት. እና ቃ.** ፴፯፡፱። ቃል ኪዳንን የሚ ያከብሩት ምህረትን ያገኛሉ፣ **ት. እና ቃ.** ፹፡፯። እኔ ጌታ ኃጥያቶችን ስለምሰርይ፣ እና ኃጥያታች ውን በትሁት ልቦች ለሚናዘዙት በምህረት የተሞ ላሁ ነኝ፣ **ት. እና ቃ.** ፵፭፡፪። እኔ ጌታ ለቅን ሁሉ ምህረት አሳያለሁ፣ **ት. እና ቃ.** ፣፲፯፡፪። እና እንደ ትንሽ ልጅ የሚቀበልህም፣ መንግስቴን ይቀበላል፣ ይማራሉና፣ **ት. እና ቃ.** ፣፲፱፡፲። ምህረት በፊት ለፊትህ ይሄዳል፣ **ሙሴ** ፯፡፴፩።

መለወጥ። *ደግሞም ኢየሱስ ክርስቶስ፤ የክህነት ቁልፎች ተመልከቱ*

የሰማይ ሰዎችን ለማየትና ክብራቸውን ለመ ቋቋም እንዲችሉ ዘንድ ሰዎች በፍጥረት እና በአ መለካከት ለጊዜአዊ የሚቀየሩበት ሁኔታ—ይህም ማለት፣ ወደ ከፍተኛ መንፈሳዊ ደረጃ ከፍ ተደር ገዋል ማለት ነው።

የክርስቶስ መለወጥ፣ ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ፣ እና ዮሐንስ በፊት ለፊታቸው ግርማዊና የተለወጠውን ጌታ አዩ። አዳኝ ከእዚህ በፊት ለጴጥሮስ የመንግ ስተ ሰማይ ቁልፎችን እንደሚቀበል ቃል ገብቶለት ነበር (ማቴ. ፲፮፡፲፫–፲፱፣ ፲፯፡፩–፱፣ ማር. ፱፡፪–፲፣ ሉቃ. ፱፡ጽ፳–፴፮፣ ፪ ጴጥ. ፩፡፲፯–፲፰)። በዚህ አስ ፈላጊ ድርጊት፣ አዳኝ፣ ሙሴ፣ እና ኢሊያ (ኤል

ያስ) ቃል የተገቡትን የክህነት ቁልፎች ለጴጥሮስ፣ ያዕቆብ፣ እና ዮሐንስ ሰጡ። በእነዚህ የክህነት ቁልፎች፣ ሐዋሪያት ኢየሱስ ካረገ በኋላ የመንግስትን ስራ ለመቀጠል ሀይል ነበራቸው።

በመለወጫ ተራራ ላይ ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ፣ እና ዮሐንስ ተለውጠው እንደነበር ጆሴፍ ስሚዝ አስተምሯል። እነርሱም ምድርን ወደፊት በተከበረችበት ሁኔታዋ የምትመስልበትን ራዕይ አዩ (ት. እና ቃ. ፹፫፡፩–፹፩)። እነርሱም የተቀየሩትን ሙሴን እና ኤልያስን አዩ እናም የአብን ድምፅ ሰሙ። አብም እንዲህ አለ፣ “በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው” (ማቴ. ፲፯፡፭)።

የተለወጡ ሰዎች፣ የእስራኤል እግዚአብሔርን አዩ፣ **ዘፀአ.** ፳፬፡፱–፲፩። እግዚአብሔር ጋር ሲነጋገር የፊቱ ቁርበት አንጸባረቀ፣ **ዘፀአ.** ፴፬፡፳፱ (ማር. ፱፡፪–፫)።

የኢየሱስ ፊትም እንደ ፀሐይ በራ፣ **ማቴ.** ፲፯፡፪ (ማር. ፱፡፪–፫)። የእስራኤል ስለ ፊቱ ክብር የሙሴን ፊት ትኩር ብለው መመልከት አልቻሉም፣ ፪ ቆሮ. ፫፡፯።

የአቢናዲ ፊት በታላቅ ብርሀን በራ፣ ሞዛያ ፲፫፡፭–፱። እነርሱም እሳት በሚመስል ነገር ተከበው ነበር፣ ሔሌ. ፭፡፳፫፣ ፴፯፣ ፵፫–፵፭ (፫ ኔፊ ፲፯፡፳፬፣ ፲፱፡፲፩)። እነርሱም እንደ ኢየሱስ ገፅታ ነጭ ነበሩ፣ ፫ ኔፊ ፲፱፡፳፭። ለእነርሱ የተለወጡ መሰላቸው፣ ፫ ኔፊ ፳፯፡፲፭።

በመንፈስ ካልተነሳሳ በስተቀር፣ ማንም ሰው በስጋ እግዚአብሔርን አላየም፣ ት. እና ቃ. ፴፯፡፲–፲፪። በመንፈስ ሀይልም አይኖቻችን ተከፈቱ፣ ት. እና ቃ. ፷፯፡፲፪።

የእግዚአብሔር ክብርም በሙሴ ላይ ነበር፣ ሙሴ ፭፡፪። ክብሩ እኔ ላይ ነበር፣ እና ፊቱን አየሁኝ፣ በእርሱ ፊት ተለወጬ ነበርና፣ ሙሴ ፭፡፲፭። ሰማያት ሲከፈቱ አየሁ፣ እና ክብር ለበሽም ነበር፣ ሙሴ ፯፡፣–፱።

መለየት። *ደግሞም* እጅን መጫን፣ ጥሪ፣ በእግዚአብሔር መጠራት፣ የተጠራበት *ተመልከቱ*

ለቅዱስ አላማዎች መመረጥ እና መቀደስ። ይህ ምደባ የሚሰጠው በቤተክርስቲያኗ ድርጅት ውስጥ ለልዩ አገልግሎት ትክክለኛው ስልጣን ባለው ሰው እጅ መጫን በኩል ነው። በሚሾሙበት ጊዜ ቁልፎች የሚቀበሉት በክህነት ስልጣን ቡድኖች ላይ ስልጣን ያሏቸው ብቻ ናቸው። ከክህነት ስልጣን ቡድኖች ፕሬዘደንት ሌላ ሀላፊነት የሚሾሙት ሰዎች የክህነት በረከትን ለመቀበል ይችላሉ፣ ነገር ግን ከበረ ከቱ ጋር ለእነርሱ ምንም ቁልፎች አይሰጧቸውም።

በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ፣ **የሐዋ.** ፲፫፡፪–፫።

ሌሎች ኤጲስ ቆጶሳት ይሾሙ፣ ት. እና ቃ. ፴፯፡፲፬። ዳኛው ኤጲስ ቆጶስ ለአገልግሎት ይሾም፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፲፯፣ ፫፬።

ሰው በትንቢትና ስልጣን ባላቸው ሰዎች እጆችን በመጫን በእግዚአብሔር መጠራት አለበት፣ ኢ.ኦ. ፭፡፭።

መላእክት

በሰማይ ውስጥ መላእክት ተብለው የተጠሩ ሁለት አይነት ህያው ፍጡር አሉ፡ መንፈሳት የሆኑ እና የስጋ እና አጥንት ሰውነቶች ያላቸው። መንፈስ የሆን መላእክት የስጋ እና አጥንት ሰውነትን አላገኙም፣ ወይም ስጋዊ ሰውነት የነበራቸው እና ትንሣኤን የሚጠብቁ መንፈሶች ናቸው። የስጋ እና አጥንት ሰውነቶች ያሏቸው መላእክት ከሞት የተነሱ ወይም በእምነት የተወሰዱ ናቸው።

በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ ስለመላእክት ስራ የሚጠቅሱ ብዙዎች አሉ። አንዳንዴ መላዕክት የእግዚአብሔር መልእክቶችን ሲያቀርቡ በመብረቅ ድምጾች ይናገራሉ (ሞዛያ ፳፯፡፲፩–፲፯)። ጻድቅም ስጋዊ ሰዎች መላዕክት ተብለው ለመጠራት ይችላሉ (ጆ.ስ.ት.፣ ዘፍጥ. ፲፱፡፲፭ [ተጨማሪ])። አንዳንድ መላእክት በሰማይ ውስጥ በእግዚአብሔር ዙፋን አጠገብ ያገለግላሉ (አልማ ፴፯፡፳፪)።

ቅዱሣት መጻህፍት ስለዲያብሎስ መላእክትም ይናገራሉ። እነዚህ ሉሲፈርን የተከተሉ እና በቅድመ ምድራዊ ህይወት ከእግዚአብሔር ፊት እንዲወጡ ተደረጉ እና ወደ ምድር ተወረወሩ (ራዕ. ፲፪፡፭–፱፣ ፪ ኔፊ ፱፡፱፣ ፲፯፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፴፯–፴፺)።

ያዕቆብ የእግዚአብሔር መላእክት ሲወጡ እና ሲወርዱ አየ፣ ዘፍጥ. ፳፰፡፲፪። የእግዚአብሔር መላእክት ያዕቆብን ተገናኙት፣ ዘፍጥ. ፴፪፡፩–፪። ጌዴዎን የእግዚአብሔርን መልአክ ፊት ለፊት አየ፣ መሳ. ፮፡፳፪። የእግዚአብሔርም መልአክ ኢየሩሳሌምን ያጠፋት ዘንድ እጁን ዘረጋ፣ ፪ ሳሙ. ፳፬፡፲፮። መላእክት ኤልያስን ነካው እና እንዲህ አለው፡ ተነስተህ ብላ፣ ፩ ነገሥ. ፲፱፡፭–፯። ዳንኤል መላእክቱ ገብርኤልን በራዕይ አየ፣ ዳን. ፰፡፲፭–፲፯። መላእክቱ ሚካኤል ዳነልን ረዳ፣ ዳን. ፣፡፲፫።

ማላእክቱ ገብርኤል ከእግዚአብሔር የተላከ ነበር፣ ሉቃ. ፩፡፲፱፣ ፳፯–፳፯። የዲያብሎስ መላእክት በእስር ለፍርድ ይጠበቃሉ፣ ይሁዳ ፩፡፮ (፪ ጴጥ. ፪፡፬)።

ሰዎች መላዕክቱ ከሰማይ ሲወርዱ ተመለከቱ፣ ፫ ኔፊ ፲፯፡፳፬። ሞሮኒ ስለ መላእክት አገልግሎት ጻፈ፣ ሞሮኒ ፯፡፳፭–፴፪።

የአሮናዊ ክህነት የመላእክትን አገልግሎት ቁልፎች የያዘ ነው፣ ት. እና ቃ. ፲፫። ሞሮኒ፣ መጥምቁ ዮሐንስ፣ ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ፣ ዮሐንስ፣ ሙሴ፣ ኤልያስ፣ እና ኢሊያ ሁሉ ጆሴፍ ስሚዝን እንደ መላ

እክት አገለገሉት፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፭–፲፪። የመ ላእክቶችን አገልግሎት ለመቋቋም አትችሉም፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፲፫። የመላእክት አለቃው ሚካ ኤል አዳም ነው፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፹፡ መላእክት ከሞት የተነሱ ሰዎች፣ የስጋ እና የአጥንት ሰውነቶች ያሏቸው ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፲፳፱። በዚህ ምድር አባል ከነበሩ ወይም ከሆኑ በስተቀር፣ የሚያገለ ግሉ መላዕክቶች አይኖሩም፣ ት. እና ቃ. ፲፴፡፭። የእግዚአብሔርን የዘለአለማዊ ጋብቻ ህግ የማያ ከብሩ ሰዎች አያገቡም ወይም አይጋቡምም ነገር ግን በሰማይ ውስጥ እንደ መላእክት ይመደባሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፴፪፡፲፯–፲፰።

መልስ መስጠት፣ ሂሳብ፣ ተጠያቂነት፣ ሀላፊነት። *ደግሞም ነጻ ምርጫ ተመልከቱ*

ጌታ ሁሉም ሰዎች ለእራሳቸው ምክንያቶች፣ ጸባያት፣ ፍላጎቶች፣ እና ስራዎች ሀላፊ ናቸው አለ።

የተጠያቂነት እድሜ ልጆች ለእራሳቸው ስራ ዎች ሀላፊ እንደሆኑ እና ኃጢያት ለመስራት እና ንስሀ ለመግባት ችሎታ እንዳላቸው የሚታሰቡበት እድሜ ነው።

እንደ መንገዱ በየሰዉ ሁሉ እፈርድባችኋለሁ፣ ሕዝ. ፲፰፡፴።

ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል፣ ማቴ. ፲፪፡፴፮። የመጋቢነ ትህን ሂሳብ አስረክበኝ፣ ሉቃ. ፲፮፡፪። እያንዳን ዳችን ስለ ራሳችን ለእግዚአብሔር መልስ እንሰጣ ለን፣ ሮሜ ፲፡፡፲፪። ሙታን እንደ ሥራቸው መጠን ተከፈሉ፣ ራዕ. ፳፡፲፪።

ቃላቶቻችን፣ ስራዎቻችን፣ እና ሀሳቦቻችን ይፈርዱብናል፣ አልማ ፲፪፡፲፡ መልካምም ይሁን መጥፎ ለማድረግ በራሳችን ላይ ፈራጅ እንሆናለን፣ አልማ ፵፭፡፲፡ ለራሳችሁ እንድት ሰሩ ተፈቅዶላችኋል፣ ሔለ. ፲፡፡ ፳፱–፴፭። ይህ ንን ነገር እንድታስተምር እልሃለሁ—ሊጠየቁበት ለሚችሉ ንሰሃ እና ጥምቀት እንደሚያስፈልጋ ቸው፣ ሞሮኒ ፰፡፲፡

ለተጠያቂነት እድሜ የደረሱ ሁሉ ንሰሃ መግባት እና መጠመቅ አለባቸው፣ ት. እና ቃ. ፲፰፡፵፪። ተጠያቂ እስኪሆኑ ድረስ ህጻናት ልጆችን ለመፈ ተን ሰይጣን አይችልም፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፵፯–፵፯። ልጆች በስምንት አመታቸው ይጠመቁ፣ ት. እና ቃ. ፳፰፡፳፯። እያንዳድኑም ሰው ለእ ራሱ ኀጥያቶች በፍርድ ቀን ተጠያቂ ይሆናል፣ ት. እና ቃ. ፲፭፡፫፰።

ጥሩ ከመጥፎ እንዲያውቁም ተሰጥቶአቸዋል፤ ስለዚህ ለእራሳቸው ሃላፊ ናቸው፣ ሙሴ ፮፡፶፮። ሰዎች ለእራሳቸው ኃጥያቶች ይቀጣሉ፣ ኢ.ኦ. ፭፡፪።

መልከ ጼዴቅ። *ደግሞም ሳሌም፤ የመልከ ጼዴቅ ክህነት ተመልከቱ*

ከጎርፍ በኋላ እና በአብርሐም ዘመን ይኖር የነበረ የብሉይ ኪዳን ታላቅ ሊቀ ካህን፣ ነቢይ እና መሪ። የሳሌም (ኢየሩሳሌም) ንጉስ፣ የሰላም ንጉስ፣ የጻ ድቅ ንጉስ፣ (ይህም የእብራውያን የመልከ ጼዴቅ ትርጉም ነው)፣ እናም የልዑል እግዚአብሔር ካህን ተብሎ ይጠራ ነበር።

አብርሐም ለመልከ ጼዴቅ አስራት ከፈለ፣ ዘፍጥ. ፲፡፡፲፰–፳። የመልከ ጼዴቅ ህዝቦች ጽድ ቅን አመጡ፣ እናም ሰማይን አገኙ፣ ጆ.ስ.ት.፣ ዘፍጥ. ፲፡፡ ፳፭–፳፡

ክርስቶስ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ሊቀ ካህን ነበር፣ ዕብ. ፭፡፮። መልከ ጼዴቅ፣ የሳሌም ንጉስ፣ የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበር፣ ዕብ. ፯፡፩–፫፡

ማንም ከመልከ ጼዴቅ በላይ ታላቅ አልነበረም፣ አልማ ፲፫፡፲፡–፲፱፡

አብርሐም ክህነትን ከመልከ ጼዴቅ ተቀበለ፣ ት. እና ቃ. ፹፡፡ ፲፡፡ ለጌታ ስም ክብር፣ የጥንት ጊዜ ቤተክርስቲያኗ ክህነትን የመልከ ጼዴቅ ክህነት ብለው ጠሩት፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፩–፱፡

መልካሙ እረኛ። *ደግሞም ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልከቱ*

ኢየሱስ ክርስቶስ መልካሙ እረኛ ነው። በም ሳሌም፣ ተከታዮቹ ኢየሱስ እንደሚጠብቃቸው በጎች ናቸው።

እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፣ መዝ. ፳፫፡፩፡ መንጋውን እንደ እረኛ ያሰማራል፣ ኢሳ. ፵፡፲፩፡ በጎቼን እፈልጋለሁ፣ ሕዝ. ፴፡፡ ፲፪፡

መልካም እረኛ እኔ ነኝ፣ ዮሐ. ፲፡፲፡–፲፭፡ ኢየ ሱስ ለበጎች ትልቅ እረኛ ነው፣ ዕብ. ፲፫፡፳፡

በጎቼንም ይቆጥራል፣ እናም እነርሱ ያውቁታል፣ ፩ ኔፊ ፳፪፡፡ ፳፭፡ መልካሙ እረኛ እናንተን ይጣራል እላችኋለሁ፣ ይህም ክርስቶስ ነው፣ አልማ ፭፡፴፰፣ ፳፡ አንድ መንጋ፣ እናም እረኛውም አንድ ይሆ ናል፣ ፫ ኔፊ ፲፭፡፳፭ (ዮሐ. ፲፡፲፯)።

መልካምነት። *በጎነት ተመልከቱ*

መልክ። *ፊት፣ መልክ ተመልከቱ*

መመሰጥ። *ማሰላሰል ተመልከቱ*

መመስከር። *ደግሞም ምስክርነት ተመልከቱ*

በመንፈስ ቅዱስ ሀይል ምስክር መስጠት፣ በግል እውቀት ወይም እምነት ስለእውነት በክብር ማወጅ።

መንፈስ እኔ ይመሰክራል፣ ዮሐ. ፲፭፡፳፮። እንድንሰብክና እንመሰክር ዘንድ አዘዘን፣ የሐዋ. ፲፡፵፪።

ሶስቱ ካዩት ስለእውነቱ ይመሰክራሉ፣ ፪ ኔፊ

ፍጷ፯፡ ፲፪። የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ወደ ሰዎች ልጆች ልብ ያደርሰዋል፣ ፪ ኄፊ ፡ ፀ፲፡ ፡ ፩። ቅዱስ መጽሐፍት ስለክርስቶስ ይመሰክራሉ፣ ያዕቆ. ፯፡ ፣ ፣–፣ ፩ (ዮሐ. ፭፡ ፡ ፀ፱)። እነዚህ የምናገራቸው ነገሮች እውነት መሆናቸውን እንደማውቅ እመሰክርላችኋለሁ፣ **አልማ** ፭፡ ፡ ፣ ፭ (አልማ ፀ፱፡ ፡ ፭)።

ስለእነርሱም በ ትግዚአብሔር ሀይል ትመሰክራላችሁ፣ ት. እና ቃ. ፣ ፯፡ ፡ ፣–፭። መንፈስ የሚመሰክርላችሁንም ሁሉ አከናውኑ፣ ት. እና ቃ. ፣ ፣ ፯፡ ፡ ፯። የላኳችሁ እንድትመሰክሩ እና ሰዎችን እንድታስጠነቅቁ ነው፣ ት. እና ቃ. ፣ ፣ ፭፡ ፣ ፣ ፩።

መመረጥ። ደግሞም መጠራት እና መመረጥ ተመልከቱ

በቅድመ ህይወት ብቁነት መሰረት፣ እግዚአብሔር የአብርሐም ዘርና የእስራኤል ቤት እንዲሁም የቃል ኪዳን ህዝብ ማን እንደሚሆን መረጠ (ዘዳግ. ፡ ፣–ፀ፣ አብር. ፪፡ ፀ–፣ ፩)። እነዚህ ሰዎች የአለም ሀገሮችን ሁሉ ለመባረክ እንዲችሉ ልዩ በረከቶች እና ሀላፊነቶች ተሰጣቸው (ሮሜ ፣ ፩፡ ፡ ፭–፯፣ ፩ ጴጥ. ፩፡ ፪፣ አልማ ፣ ፣፡ ፡ ፩–፭፣ ት. እና ቃ. ፣ ፣ ፡ ፣ ፣)። ነገር ግን፣ እነዚህ የተመረጡትም ደህንነትን ለማግኘት ዘንድ በዚህ ህይወት መጠራት እና መመረጥ አለባቸው።

መመኘት። ደግሞም ቅናት ተመልከቱ

በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ እንደሚጠቀሙት፣ መመኘት በሰው መቅናት ወይም ለአንድ ነገር ከመጠን በላይ የሆነ ፍላጎት መኖር ነው።

አትመኝ፣ **ዘፀአ.** ፭፡ ፣ ፣ (ዘዳግ. ፡ ፡ ፭ ፣ ሞዛያ ፣ ፡ ፡ ፩ ፣ ት. እና ቃ. ፣ ፣ ፡ ፭ ፡) ግፍን የሚጠላ ግን ብዙ ዘመን ይኖራል፣ ምሳ. ፭ ፡ ፣ ፣ ። በእርሻው ላይ ይመኛሉ፡ ይነጥቃሉ፣ ሚክ. ፪፡ ፪።

ከመጐምጀትም ሁሉ ተጠበቁ፣ ሉቃ. ፣ ፪፡ ፣ ፡ ። ህጉ አይመኝ አለ፣ ሮሜ ፣ ፣ ። በመጨረሻው ቀናት ሰዎች ትምክህተኞች ይሆናሉ፣ ፪ ጢሞ. ፡ ፡ ፩–፪።

ላባን ንብረታችንን ሲያይ፣ ተመኘው፣ ፩ ኄፊ ፡ ፭ ፡ ።

የራስህን ንብረት አትመኝ፣ ት. እና ቃ. ፣ ፣ ፡ ፭ ። ትምክህተኞች አትሁኑ፣ ት. እና ቃ. ፣ ፣ ፡ ፣ ፡ ። የወንድማችሁ የሆነውን አትመኙ፣ ት. እና ቃ. ፣ ፣ ፡ ፭ ።

መማል። መሀላ፣ መስደብ፣ ማራከስ ተመልከቱ

መማረክ። ባርነት ተመልከቱ

መማር። ይቅርታ ማድረግ ተመልከቱ

መምህር፣ የአሮናዊ ክህነት። ደግሞም አሮናዊ ክህነት ተመልከቱ

የአሮናዊ ክህነት ሀላፊነት።

የመምህር ሀላፊነት ቤተክርስቲያኗን መጠበቅ ነው፣ ት. እና ቃ. ፭ ፡ ፣ ፡ ። የመምህር ሀላፊነትም ከዳግማዊ ክህነት ጋር አስፈላጊ ሆኖ የተያያዘ ነው፣ ት. እና ቃ. ፡ ፡ ፣ ፣ ፣ ። የመምህር ቡድን ፕሬዘደንት ሀላፊነት ሀያ አራት መምህራንን ይመራል፣ ት. እና ቃ. ፣ ፣ ፡ ፣ ።

መምረቅ፣ ብፁዓን። መባረክ፣ የተባረከ፣ በረከት ተመልከቱ

መምረጥ፣ መረጠ፣ የተመረጠ (ግስ)። ደግሞም ነጻ ምርጫ፣ ነጻ፣ ነጻነት፣ ጥሪ፣ በእግዚአብሔር መጠራት፣ የተጠራበት ተመልከቱ

ጌታ ግለሰብን ወይም ቡድንን በሚመርጥበት ወይም በሚወስንበት ጊዜ፣ ደግሞም በአብዛኛው ጊዜ እነርሱን እንዲያገለግሉ ይጠራል።

የምታገለግለውን ዛሬ ምረጡ፣ **ኢያ.** ፡ ፣ ፡ ፣ ፡ (አልማ ፡ ፡ ፡ ሙሴ ፣ ፡) በመከራም እቶን መርጨሀለሁ፣ ኢሳ. ፡ ፡ ፣ ፡ ፣ (፩ ኄፊ ፡ ፣)።

የተጠሩ ብዙዎች፡ የተመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸው፣ ማቴ. ፣ ፣ ፡ ፣ (ማቴ. ፡ ፣ ፣ ፣ ፡ ፣ ፣ ፡ ፣ ፡ ፣ ፡ ፣) ። እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም፣ ዮሐ. ፣ ፣ ፣ ። እግዚአብሔር ጥበበኞችን እንዲያሳፍር የዓለምን ሞኝ ነገር መረጠ፣ ፩ ቆሮ. ፩ ፡ ፣ ። ዓለም ሳይፈጠር በፊት መርጦናል፣ ኤፌ. ፩ ፡ ፡ ።

ነፃነትን ወይም ዘለዓለማዊ ህይወትን ለመምረጥ፣ ወይም ምርኮንና ሞትን ለመምረጥ ነፃ ነን፣ ፪ ኄፊ ፪ ፡ ፣ ።

የተከበሩትና ታላቆቹ በመጀመሪያ ተመርጠው ነበር፣ ት. እና ቃ. ፣ ፣ ፡ ፣ ፡ ፣–ፀ ።

እስራኤል በእግዚአብሔር ተመርጣ ነበር፣ ሙሴ ፩ ፡ ፣ ።

አብርሐም ከመወለዱ በፊት ተመርጦ ነበር፣ **አብር.** ፣ ፡ ፣ ፣ ።

መምከር (ግስ)

በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ እንደሚጠቀሙበት፣ መምከር ማለት ምክር መስጠት ወይም ማስተማር ማለት ነው።

በእሳት የነጠረውን ወርቅ ከእኔ ትገዛ ዘንድ እመክርሀለሁ፣ ራዕ. ፣ ፡ ፣ ፡ ።

ጌታን ለመምከር አትፈልግ፣ ያዕቆ. ፣ ፡ ፣ ። በስራዎቼ በሙሉ በጥበብ ይመክራል፣ **አልማ** ፣ ፡ ፣ ፡ ፣ ።

ኃጥያቶቻችሁ ወደ እኔ መጥተዋል ምክንያቱም በገዛ መንገዳችሁ ምክርን ትፈልጋላችሁና፣ ት. እና ቃ. ፣ ፣ ፡ ፣ ፣ ።

መስረቅ

ከሌላ ሰው ነገርን በመዋሸት ወይም በወንጀል መውሰድ። ጌታ ልጆቹን እንዳይሰርቁ ሁልጊዜም

ያዝዛቸዋል (ዘፀአ. ፳፰፡፲፭፣ ማቴ. ፲፱፡፲፰፣ ፪ ኔፊ ፳፯፡፴፪፣ ሞዛያ ፲፫፡፳፪፣ ት. እና ቃ. ፶፱፡፯)።

ሌቦችም ቆፍረው በማይሠርቁት ዘንድ ለእናንተ በሰማይ መዝገብ ሰብስቡ፣ ማቴ. ፮፡፲፱–፳፩።

የኔፋውያን መሽነፍ የመጣው በልባቸው ኩራት፣ እጅግ ሀብታም በመሆናቸው በመዝረፋቸው፣ በመስረቃቸው የተነሳ ነው፣ ሔሊ. ፬፡፲፪።

የሚሰርቅ እና ንስሃ የማይገባ ወደውጭ ይጣላል፣ ት. እና ቃ. ፵፪፡፳። ከሰረቀ ወይም ከሰረቀች፣ ለም ድርሪታ ሕግ በማሳለፍ ይሰጣል ወይም ትሰጣለች፣ ት. እና ቃ. ፵፪፡ ፹፬–፹፭።

መሰረታዊ መመሪያ። ደግሞም ወንጌል ተመልከቱ

መሰረታዊ ትምህርት፣ እውነት፣ ወይም ህግ። የወንጌሉ ቀዳሚ መሰረታዊ መርሆች በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እምነት እና ንስሐ መግባት ነው (ኢ.አ. ፩፡፬)።

የክርስቶስን ነገር መጀመሪያ የሚናገረውን ቃል ትተን ወደ ፍጻሜ እንሂድ፣ ጆ.ስ.ት.፣ ዕብ. ፮፡፩።

የዚች ቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች፣ ካህናት እና መምህራን የወንገሌ ሙላት በሚገኝበት በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ ያስተምራሉ፣ ት. እና ቃ. ፵፪፡፲፪። በመሰረታዊ መመሪያ፣ በትምህርት፣ በሁሉም ነገሮች፣ በፍጹም ተማሩ፣ ት. እና ቃ. ፹፰፡ ፹፱ (ት. እና ቃ. ፶፯፡፲፭)። ሁሉም ሰው በሰጠሁት ስነምግባር ምርጫ መሰረት፣ በትምህርትና በመሰረታዊ መርሆች ይስራ፣ ት. እና ቃ. ፻፩፡ ፹፯፡፹።

በዚህ ህይወት የምናገኘው ማንኛውም የመረዳት ችሎታ ደረጃ፣ ይህም ከሞት ስንነሳ አብሮን ይነሳል፣ ት. እና ቃ. ፻፴፡ ፲፡–፲፪።

መሰቀል። ደግሞም መስቀል፣ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ፣ ኅልኅታ ተመልከቱ

በብሉይ ኪዳን ጊዜዎች ውስጥ ልምድ የነበረ፣ ሮሜ የምትጠቀምበት የመግደያ ዘዴ፣ በዚህም ሰው እጆቹን እና እግሮቹን በመስቀል ላይ በማሰር ወይም በምስማር በመምታት ይገደላል። ይህም በልምድ የሚደረገው ለባሪያዎችና ለትንሽ ወንጀለኞች ነው። ከመሰቀል አስቀድሞ በልምድ መገረፍ ነበር (ማር. ፲፭፡፲፭)። የሚሰቀለው ሰው በልምድ የእራሱን መስቀል ወደ ሚሰቀልበት ቦታ እንዲሸከም ይደረጋል (ዮሐ. ፲፱፡፲፯–፲፯)። በልምድም ልብሱን ፍርዱን የሚፈፅሙ ወታደሮችም ይወስዱታል (ማቴ. ፳፯፡፴፭)። የሰውየው እግሮች ከም ድር ሰላሳ ሰንቲ ሜትር ወይም ስልሳ ሰንቲ ሜትር በላይ እንዲሆን ዘንድ መስቀሉም በመሬት ውስጥ ይቀበራል። በመስቀሉ ላይ ያለው ሰው እስከሚ ሞትም ድረስ መስቀሉ በወታደሮች ይጠበቃል፣ ይህም አንዳንዴ እስከ ፫ ቀናት ይፈጃል (ዮሐ. ፲፱፡ ፴፩–፴፯)።

ኢየሱስ የተሰቀለው የማያምኑ ቡድኖች በቁሳር ላይ እንዳመጸና የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ስላለም እንደተሳደበ በሀሰት በመክሰሳቸው ምክንያት ነበር። ቀይ ልብስ(ዮሐ. ፲፱፡ ፪)፣ የእሾኽ አክሊል፣ እና ሌሎች ስድቦች በኢየሱስ ላይ ተደርገው ነበር (ማቴ. ፳፯፡ ፳፱፣ ማር. ፲፭፡ ፳፭)።

ክፉዎች የመሲህን እጆችና እግሮች ይበሳሉ፣ መዝ. ፳፪፡ ፲፩–፲፳። ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት ይሄዳል፣ ኢሳ. ፶፫፡ ፯።

ኢየሱስ ስለመሰቀሉ አስቀድሞ ተናገረ፣ ማቴ. ፳፡ ፲፱–፲፱። የክርስቶስ መሰቀል ተገለጸ፣ ማቴ. ፳፯፡ ፳፪–፶ (ማር. ፲፭፡ ፳፪–፴፯፣ ሉቃ. ፳፫፡ ፳፯–፶፮፣ ዮሐ. ፲፱፡ ፲፯–፴)።

ኔፊ በራዕይ የክርስቶስን ስቃይና መሰቀል አየ፣ ፩ ኔፊ ፲፩፡ ፴፫። ኔፊ ስለ ክርስቶስ ስቃይና መሰቀል ተናገረ፣ ፩ ኔፊ ፲፱፡ ፱–፲፱። ያዕቆብ ስለእስራኤል ቅዱስ አገልግሎት እና መሰቀል ተናገረ፣ ፪ ኔፊ ፮፡ ፱። በአሜሪካ ውስጥ ሀይለኛ ንፋሶች፣ የምድር መንቀጥቀጥ፣ እሳቶች፣ አውሎ ንፋሶች፣ ክርስቶስ በኢየሩሳሌም ውስጥ እንደተሰቀለ መሰከሩ፣ ፫ ኔፊ ፰።

እኔም የተሰቀልኩት ኢየሱስ ነኝ፣ ት. እና ቃ. ፵፭፡ ፹፩–፹፪። በእስር ቤት ላሉት መንፈሳት ክርስቶስ ያገለገለበት ጊዜ በሞቱ እና በትንሳኤው ጊዜ መካከል የተገደቡ ነበሩ፣ ት. እና ቃ. ፻፴፰፡ ፳፯።

መሰዊያ። ደግሞም መስዋዕት ተመልከቱ

ለመስዋዕት፣ ለቁርባን፣ እና ለአምልኮ የሚጠቀሙበት መሳሪያ።

ኖኅም ለእግዚአብሔር መሠውያውን ሠራ እና መሥዋዕትን አቀረበ፣ ዘፍጥ. ፰፡ ፳። አብራም መሠውያን ለእግዚአብሔር ሠራ፣ ዘፍጥ. ፲፪፡ ፯–፰። አብርሐም ልጁን ይስሐቅንም አስሮ በመሠዊያው በእንጨቱ ላይ አጋደመው፣ ዘፍጥ. ፳፪፡ ፱ (ዘፍጥ. ፳፪፡ ፩–፲፫)። ያዕቆብ በዛም መሰዊያ ሰራ እና ቦታውንም ቤቴል ብሎ ጠራ፣ ዘፍጥ. ፴፭፡ ፮–፯። ኤልያስ መሰዊያ ሰራ እና የበአል ቄሶችን እንዲፎካ ከሩት ጠየቃቸው፣ ፩ ነገሥ. ፲፰፡ ፲፯–፴።

መባህን በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ፣ አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ፣ ማቴ. ፭፡ ፳፫–፳፬። ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ጠበቁት ምስክር የታረዱትን የሰዎች ነፍሳት ከመሠዊያ በታች አየሁ፣ ራዕ. ፮፡ ፱ (ት. እና ቃ. ፻፴፭፡ ፯)።

ሌሒ የድንጋይ መሠዊያን ሠራ እና ለጌታ ለአምላካችን ምስጋና አቀረበ፣ ፩ ኔፊ ፪፡ ፯።

አብርሐም ከኤልከናኽ መሰዊያ ላይ ከሞት ድኖ ነበር፣ አብር. ፩፡ ፳–፳፩።

መሲህ። *ደግምም ኢየሱስ ክርስቶስ፤ የተቀባውን ተመልከቱ*

በዕብራውያን እና በአራሚያክ ቋንቋ ይህ ቃል “የተቀባ” ማለት ነው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ተብሎ ተጠርቷል፣ ይህም በግሪክ ቋንቋ *መሲህ* ማለት ነው። ይህም የተቀባ ነቢይ፣ ካህን፣ ንጉስ፣ እና መምጣቱን አይሁዶች በጉጉት ይጠብቁት የነበረ አዳኝ ማለት ነው።

ብዙ አይሁዶች ከሮሜ ሀይል የሚያድናቸውን እና ታላቅ የሀገር ብልፅግናን ብቻ ይጠብቁ ነበር፤ በዚህም መሲህ ሲመጣ፣ መሪዎች እና ብዙ ሌሎች አስወገዱት። ትሁት እና ታማኝ የሆኑት ብቻ የናዝሬት ኢየሱስ እውነተኛው ክርስቶስ እንደሆነ ለማየት ችለው ነበር (ኢሳ. ፶፫፣ ማቴ. ፲፮፡፲፯፣ ዮሐ. ፱፡፳፭–፳፯)።

መሲሕ መንፈስ ይኖረዋል፣ ወንጌልን ይሰብካል፣ እና ነጻነትን ያውጃል፣ ኢሳ. ፷፩፡፩–፫ (ሉቃ. ፬፡፲፰–፳፩)።

መሢሕን አግኝተናል አለው፤ ትርጓሜውም ክርስቶስ ማለት ነው፣ ዮሐ. ፩፡፵፩ (ዮሐ. ፬፡፳፭–፳፮)።

ጌታ እግዚአብሔር ከአይሁዶች መካከል መሲሁን ወይም በሌላ አነጋገር መድኃኒት ያስነሳል፣ ፮ ኔሬ ፲፡፴። የእግዚአብሔር ልጅ የሚመጣው መሲሁ ነው፣ ፮ ኔሬ ፲፡፲፯። ቤዛነት በቅዱሱ መሲህ እና በእርሱ አማካይነት ይመጣል፣ ፪ ኔሬ ፪፡፮። መሲሁ በዘመን ፍፃሜ ይመጣል፣ ፪ ኔሬ ፪፡፳፮። መሲሁ ከሞት ይነሳል፣ ፪ ኔሬ ፳፭፡፲፬። አሮናዊ ክህነትን በመሲሁ ስም ለእናንተ እሰጣችኋለሁ፣ ት. እና ቃ. ፲፫። ጌታ እንዲህ አለ፡ እኔ የፅዮን ንጉስ፣ መሲሕ ነኝ፣ ሙሴ ፯፡፶፫።

መስቀል። *ደግምም መሰቀል፤ ቅዱስ ቁርባን፤ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ፤ ጎልጎታ ተመልከቱ*

ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት እንጨት (ማር. ፲፭፡፳–፳፮)። አሁን በአለም ውስጥ ብዙዎች ይህን እንደ ክርስቶስ መሰቀልና ስለኃጢያት ዋጋ መክፈሉ ምልክት አድርገው ያስቡበታል፤ ነገር ግን ጌታ ለተሰቀለበትና ለመስዋዕቱ የእራሱን ምልክት መስበር ቷል—ይህም የቅዱስ ቁርባን ዳቦና ውሀ ነው (ማቴ. ፳፮፡፳፮–፳፰፣ ት. እና ቃ. ፳፡፶፣ ፫፭–፫፱)። በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ፣ መስቀላቸውን የሚያነሱ ኢየሱስ ክርስቶስን በጣም ወድደው ኃጢያተኝነታቸውንና ምድራዊ ፍላጎታቸውን ይክዳሉም፣ የእግዚአብሔርንም ትእዛዛት ያከብራሉ(ጆ.ስ.ት.፣ ማቴ. ፲፮፡፳፭–፳፮ [ተጨማሪ])።

መስቀሉንም ተሸክመህ ና፡ ተከተለኝ፣ ማር. ፲፡፳፭ (ቮ ኔሬ ፲፪፡፴፣ ት. እና ቃ. ፳፫፡፮)። ኢየሱስ በመስቀል ታግሦ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአል፣ ዕብ. ፲፪፡፪።

በመስቀል ላይ ተሰቀለ እና ለአለም ኃጢያቶች ተገደለ፣ ፮ ኔሬ ፲፩፡፴፫። የአለም መስቀሎችን የታገሱ የእግዚአብሔርን መንግስት ይወርሳሉ፣ ፪ ኔሬ ፱፡፲፰። አባቴ እንድሰቀል ዘንድ ላከኝ፣ ፫ ኔሬ ፳፯፡፲፬–፲፭።

መስቀሉን የማያነሳ፣ የማይከተለኝ፣ እናም ትእዛዛቴን የማያከብር፣ እርሱም አይድንም፣ ት. እና ቃ. ፶፮፡፪።

የሰው ልጅ በመስቀል ላይ ሲሰቀል ተመልከት፣ ሙሴ ፯፡፶፭።

መስበክ። *ደግሞም ወንጌል፤ የሚስዮን ስራ ተመልከቱ*

የወንጌል መሰረታዊ መመሪያ ወይም የትምህርት ማስተዋልን በይበልጥ ለማቅረብ የሚሰጥ መልእክት።

እግዚአብሔር ለድሆች የምሥራችን እሰብክ ዘንድ እግዚአብሔር ቀብቶኛል፣ ኢሳ. ፷፩፡፩ (ሉቃ. ፬፡፲፰–፳፩)። ተነሥተህ ወደ ነነዌ ሂድ፡ ስበክላት፣ ዮና. ፫፡፪–፣።

ከዚያ ዘመን ጀምሮ ኢየሱስ ይሰብክ ጀመር፣ ማቴ. ፬፡፲፯። ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ፣ ማር. ፲፮፡፲፭። የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን፣ ፮ ቆሮ. ፩፡፳፪–፳፬። በእርሱም ደግሞ ሄዶ በወኅኒ ለነበሩ ነፍሳት ሰበከላቸው፣ ፮ ጴጥ. ፫፡፲፱።

በጌታ ፍርሃት ያለማቋረጥም ይጠበቁ ዘንድ ካነሳሳቸው በስተቀር ምንም የለም፣ ኢኖስ ፩፡፳፫። ንስሃንና እምነትን ካልሆነ በቀር ምንም እንዳያስተምሩ አዘዛቸው፣ ሞዛያ ፲፰፡፳፡ ፳። የቃሉ መሰበክ ህዝቡ ትክክለኛውን እንዲሰራ የሚመራ ታላቅ ዝንባሌ አለው፣ አልማ ፴፩፡፩።

እስከምትጠራ ድረስ እንድትሰብክ እንደተጠራህ አታስብ፣ ት. እና ቃ. ፲፩፡፲፩። ካልተሾመ በስተቀር፣ ለማንም ወንጌሌን እንዲሰብክ እንዲገንባ አይሰጠውም፣ ት. እና ቃ. ፵፪፡፲፩። ወንጌል ለእያንዳንድ ሕዝብ ይሰበክ፣ ት. እና ቃ. ፻፴፫፡፴፯፡ ፴፯።

ወንጌሉ ከመጀመሪያው ጊዜ ጀምሮ መሰበክ ጀመረ፣ ሙሴ ፭፡፶፭።

መስከር፣ ሰካራ። *የጥበብ ቃል ተመልከቱ*

መስዋዕት። *ደግምም ቅዱስ ቁርባን፤ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ፤ የተሰበረ ልብ፤ ደም ተመልከቱ*

በጥንት ቀናት፣ *መስዋዕት* ማለት አንድ ነገርን ወይም አንድ ሰውን ቅዱስ ማድረግ ማለት ነው። አሁን ይህም የአለም ነገሮችን ለጌታ እና ለመንግ

ስቱ መተው ወይም መሰቃየት ማለት ነው። የጌታ ቤተክርስቲያን አባላት ሁሉንም ነገሮች ለጌታ መስ ዋዕት ለማድረግ ፈቃደኛ መሆን ይገባቸዋል። ጆሴፍ ስሚዝ እንዳስተማረው፣ “የሁሉንም ነገሮች መስዋ ዕት የማይጠይቅ ሀይማኖት ወደ ህይወት እና ደህን ነት የሚመራ እምነትን ለመስራት ብቁ ሀይል አይ ኖረውም።” በዘለአለማዊ አስተያየት፣ በመስዋዕት የሚገኙት በረከቶች ከሚተወው ነገር ሁሉ በላይ ታላቅ ናቸው።

አዳም እና ሔዋን ከዔድን ገነት ተጥለው ከወጡ በኋላ፣ ጌታ የመስዋዕት ጅግን ሰጣቸው። ይህም ህግ የመንጋቸውን በኩራት በመስዋዕይ ማቅረብን በተ ጨማሪ ይጠብቃል። ይህም መስዋዕት በእግዚአብ ሔር አንድያ ልጅ የሚደረገው መስዋዕት ምሳሌ ነው (ሙሴ ፮፡፡፱–፳)። ይህ ልምድ እስከ ኢየሱስ ሞት ድረስ ቀጠለ፣ የእርሱ ሞትም የእንስሣት መስዋ ዕትን እንደ ወንጌል ስነስርዓት አቆመው (አልማ ፴፬፡፲፫–፲፰)። ዛሬ በቤተክርስቲያኗ ውስጥ አባላት የቅዱስ ቁርባንን ዳቦ እና ውሀ የኢየሱስ ክርስቶ ስን መስዋዕት በማስታወስ ይቀበላሉ። አሁን የክር ስቶስ ቤተክርስቲያን አባላት እንደ መስዋዕት የተ ሰበረ ልብን እና የተዋረደ መንፈስን ደግመው እን ዲያቀርቡ ተጠይቀዋል (ቮ ኔፊ ፱፡፲፱–፳፪)። ይህም እነርሱ ትሁት፣ ንስሀ የገቡ፣ እና የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ለማክበር ፈቃደኞች ናቸው ማለት ነው።

አብርሃምም ልጁን ይስሐቅንም አስሮ በመሠዊ ያው በእንጨቱ ላይ አጋደመው፣ ዘፍጥ. ፳፪፡፩–፲፰ (ያዕቆ. ፬፡፭)። የሚቃጠለውንና መሥዋዕት ህን ሠዋበት፣ ዘፀአ. ፳፡፳፬። የሚሰዋው እንስሳ እን ከን የሌለው ይሁን፣ ዘዳግ. ፲፭፡፲፱–፳፩። መታ ዘዝ ከመሥዋዕት ይበልጣል፣ ፩ ሳሙ. ፲፭፡፳፪።

መውደድ ከሚቃጠል መሥዋዕትና ከሌላው መሥዋዕት ሁሉ የሚበልጥ ነው፣ ማር. ፲፪፡፴፪–፴፫። በኢየሱስ ክርስቶስ መስዋዕት በኩል ተቀድ ሰናል፣ ዕብ. ፲፡፲–፲፡፡

ኢየሱስ እራሱን ለኃጢያት መስዋዕት አቀረበ፣ ፪ ኔፊ ፪፡፯–፯። ታላቅ እና የመጨረሻ መስዋዕት፣ አዎን መጨረሻ የሌለው እንዲሁም ዘለአለማዊ፣ የእግዚአብሔር ልጅ ነው፣ አልማ ፴፬፡፭–፲፡ ከእ ንግዲህ ደምን በማፍሰስ አታብረክቱልኝም፣ ለእግ ዚአብሔር መስዋእት የተሰበረ ልብ እናም የተዋረደ መንፈስ ታቀርባላችሁ፣ ቮ ኔፊ ፱፡፲፱–፳ (መዝ. ፶፩፡፲፯–፲፯፣ ት. እና ቃ. ፶፱፡፰)።

አሁን የመስዋዕት ቀን ነው፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፳ (ት. እና ቃ. ፶፯፡፲)። ፳ቃል ኪዳናቸውን በመ ስዋዕት ለመከተል ፈቃደኛ የሆኑት ሁሉ፣ በእኔ ተቀባይ ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፶፯፡፳። ጆሴፍ ኤፍ ስሚዝ እንደ እግዚአብሔር ልጅ አይነት ታላቅ መስዋዕት ያቀረቡት፣ ጻድቅ ነፍሶችን ተመለ ከቱ፣ ት. እና ቃ. ፲፱፳፡፲፫። ቤዛነት በእግዚአ ብሔር ልጅ መስዋዕት በኩል መጣ፣ ት. እና ቃ. ፲፱፳፡፴፭።

መስዋዕት ማቅረብ። በኩራት *ተመልከቱ*

መስደብ። *ደግሞም ማራከስ*፣ *ይቅርታ የሌለው ኃጢያት ተመልከቱ*

ወደ እግዚአብሔር ወይም ወደ ቅዱስ ነገሮች ክብር በማጣት ወይም አክብሮት ባለመኖር መናገር። ኃጥያቶችን ለማሰረየት መብት ይገባኛል ስላለ (ማቴ. ፱፡፪–፫፣ ሉቃ. ፭፡፳–፳፩)፣ እራሱን የእ ግዚአብሔርን ልጅ ብሎ ስለጠራ (ዮሐ. ፲፡፳፪–፴፮፣ ፲፱፡፯)፣ እና እርስን በሀይል ቀኝ ስቀመጥ እና በሰማይ ደመና ስመጣ ታዩኛላችሁ ስላላቸው (ማቴ. ፳፮፡፳፬–፳፭) አይሁዶች ኢየሱስ ስድብ ተናግሯል በማለት በብዙ ጊዜ ከሰውት ነበር። ያላ ቸውን ነገሮች በሙሉ ባይሆን ኖሮ እነዚህ ክሶች እውነት ይሆኑ ነበር። በሳንሀድሪን ፊት ለፍርድ በቀ ረበበት ጊዜ በሀሰት ምስክሮች የተከሰሰበትም (ማቴ. ፳፮፡፹፱–፳፭) የእግዚአብሔርን ቤተመቅደስ ተሳድ ቧል የሚል ነበር ስለክርስቶስ ፍጹም የሆነ እውቀ ትን ከመቀበል በኋላ በፍልጎት መካድ የሆነው መን ፈስ ቅዱስን መስደብ ይቅርታ የሌለው ኃጢያት ነው (ማቴ. ፲፪፡፴፩–፴፪፣ ማር. ፫፡፳፯–፳፱፣ ት. እና ቃ. ፲፴፪፡፳፯)።

የጌታን ስም የሰደበ ይገደላል፣ ዘሌዋ. ፳፬፡፲–፲፮።

የጌታ ጠላቶች ስሙን እንዲሰድቡ አይተዉም፣ ት. እና ቃ. ፲፭፡፲፭። ጌታን በሚሰድቡ ላይ በቀል ይመጣባቸዋል፣ ት. እና ቃ. ፲፲፪፡፳፬–፳፮።

መስገድ። *ማምለክ ተመልከቱ*

መሸፈን። *ዐይነ-እርግብ ተመልከቱ*

መሾም፣ *ሹመት*። *ደግሞም ሀላፊነት*፣ *ሀላፊ*፣ *ስልጣን*፣ *እጅን መጫን*፣ *ክህነት*፣ *ጥሪ*፣ *በእግዚአብሔር መጠራት*፣ *የተጠራበት ተመልከቱ*

ስልጣን ወይም ሀላፊነትን መመደብ ወይም መስ ጠት። በጌታ ቤተክርስቲያን ውስጥ በስልጣን ለመ ጠቀም፣ ሰው በእግዚአብሔር፣ በትንቢት፣ እና ስልጣን ባላቸው በእጆች በመጫን መጠራት አለ በት (እ.አ. ፩፡፳)። ምንም እንኳን ሰው በመሾም ስልጣንን ለማግኘት ቢችልም፣ ለዚህ ስልጣን ልዩ ቁልፍ ባላቸው መመሪያ ነው የሚጠቀምበት።

ለአሕዛብም ነቢይ አድርጌሃለሁ፣ ኤር. ፩፡፭።

እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣች ሁኝም፣ ሾምኋችሁ፣ ዮሐ. ፲፭፡፲፮።

ከእግዚአብሔር ስልጣን ኖሮት ካህናትን ሾመ፣ ሞዛያ ፲፰፡፲፰። ሰዎች በከፍተኛው ክህነት በቅዱስ

ስነስርዓቶች ተሾሙ፣ **አልማ** ፲፫፡፩–፱። ኢየሱስ አስራሁለቱን ሐዋርያት ጠራቸው እናም ስልጣንን ሰጣቸው፣ ፫ ኔፊ ፲፪፡፩። ሽማግሌዎች ካህናትን እና መምህሮችን እጆችን በመጫን ሾሙ፣ **ሞሮኒ** ፮።

ስላልተሾማችሁ ለትንሽ ጊዜ መቆየት አለባችሁ፣ ት. እና ቃ. ፭፡፲፯። ጆሴፍ ስሚዝ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋሪያ እንዲሆን ተሾመ፣ ት. እና ቃ. ፳፡፪ (ት. እና ቃ. ፳፯፡፲፪)። ካለቤተክርስቲያኗ ምርጫ ማንም ሰው በቤተክርስቲያን ሀላፊነት አይሾምም፣ ት. እና ቃ. ፳፡፳፮። ስልጣን ባለው ካልተሾመ በስተቀር፣ ለማንም ወንጌሌን እንዲሰብክ አይሰጠውም፣ ት. እና ቃ. ፵፪፡፲፩። ሽማግሌዎች ወንጌልን ለመስበክ ተሹመዋል፣ ት. እና ቃ. ፶፡፲፫–፲፳። የቤተክርስቲያኗን ሌሎች ሀላፊዎች መሾም እና ማስተካከልም የአስራ ሁለቱ ሀላፊነት ነው፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፶፯።

የአባቶችን በረከቶች ለማግኘት እና ይህን ንም ለማስተዳደር መብትም ለማግኘት ለመሾም ፈለኩኝ፣ **አብር.** ፩፡፪። ጆሴፍ ስሚዝ እና ኦሊቨር ካውደሪ እርስ በራስ ወደ አሮናዊ ክህነት ተሾሙ፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፳፳–፳፪።

መራመድ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መራመድ (መሄድ)። ደግምም መንገድ፣ ታዛዥነት፣ ታዛዥ፣ መታዘዝ፣ ጻድቅ፣ ጽድቅ ተመልከቱ

ከእግዚአብሔር ትምህርቶች ጋር መስማማት ወይም እግዚአብሔር ህዝቦቹ እንዲኖሩ በሚፈል ግበት መንገድ መኖር፣ ለመንፈስ ቅዱስ መነሳሳት ተቀባይ መሆን እና ታዛዥ መሆን።

በሕጌ ይሄዱ ወይም አይሄዱ እንደሆነ እኔ እን ድፈትናቸው፣ **ዘፀአ.** ፲፮፡፬። በቅንነት የሚሄዱትን ከመልካም ነገር አያሳጣቸውም፣ **መዝ.** ፹፬፡፲፩። በትእዛዜ የሚሄዱ እና ፍርዴን የሚጠብቁ፣ እነር ሱም ሕዝብ ይሆኑኛል፣ **ሕዝ.** ፲፩፡፳–፳፩ (ዘዳግ. ፳፡፲)። እግዚአብሔርም ከአንተ ዘንድ የሚሻው ምንድር ነው? ከአምላክህም ጋር በትሕትና ትሄድ ዘንድ ነው፣ **ሚክ.** ፮፡፰ (ት. እና ቃ. ፲፩፡፲፪)።

እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን እንሂድ፣ **፩ ዮሐ.** ፩፡፯ (፪ ዮሐ. ፩፡፯፣ ፫ ዮሐ. ፩፡፬፣ ፬ ኔፊ ፩፡፲፪)።

ወደ ህይወት በሚያመራው በቀጭኑ ጎዳና ካልተ ራመዱ፣ ፪ ኔፊ ፴፫፡፱። በእግዚአብሔር ፊት በን ጹህ ህሊና ተመራመድ፣ **ሞዛያ** ፪፡፳፯። በእርሱ ፊት እንከን የሌላችሁ በመሆን ተራመዱ፣ **አልማ** ፯፡፳፪።

የቤተክርስቲያን አባላት አምላካዊ አካሄድ እና ንግግር ብቁ መሆናቸውን ያሳዩ፣ ት. እና ቃ. ፳፡፳፱። በነቢዩን አድምጡ እናም ፈቴ በቅድ ስና ተራመዱ፣ ት. እና ቃ. ፳፭፡፱። ልጆቻቸውን በጌታ ፊት በቅንነት እንዲራመዱም ያስተምሩ፣ ት. እና ቃ. ፳፳፡፳፳።

አንተም ከእኔ ጋር ሁን፣ እና እኔም ከአንተ ጋር፣ ስለዚህ ከእኔ ጋር ሄድ፣ **ሙሴ** ፮፡፴፭።

መርከብ። *ደግምም ቀስተ ዳመና፣ ኖኅ፣ የመፅሐፍ ቅዱስ የአባቶች አለቃ፣ የኖኅ ዘመን የጥፋት ውሀ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ በታላቁ የጥፋት ውሀ ጊዜ ህይወትን ለማዳን በኖኅ የተገነባው መርከብ።

ከነፈር እንጨት መርከብን ለአንተ ሥራ፣ **ዘፍጥ.** ፮፡፲፬። መርከቢቱም በአራራት ተራሮች ላይ ተቀ መጠች፣ **ዘፍጥ.** ፰፡፬።

የያሬዳውያን ጀልባዎቻቸው እንደ ኖህ መርከ ብም የጠበቁ ነበሩ፣ **ኤተር** ፮፡፯።

መቀባት። *ደግምም ለታመሙት አገልግሎት መስጠት፣ ዘይት ተመልከቱ*

በጥንት ጊዜያት፣ የጌታ ነቢያት እንደ አሮን ወይም ካህናት ወይም እስራኤልን የሚገዙትን ንጉሶች አይነት ልዩ ሀላፊነቶች የሚያከናውኑትን በዘይት ይቀቡ ነበር። በዛሬ ቤተክርስትያን ውስጥ፣ መቀባት ማለት ትንሽ የተቀደሱ ዘይትን በሰው ጭን ቅላት ላይ እንደ ልዩ በረከት ክፍል ማስቀመጥ ነው። ይህም መደረግ የሚቻለው በመልከ ጼዴቅ ክህነት ሀይል እና ስልጣን በኩል ብቻ ነው። ከቅባት በኋላ፣ የእዛ አይነት ክህነት ያለው ሰው ቅባትን ያትማል እና ልዩ በረከት ለተቀባው ይሰጣል።

እንዲያገለግሉኝ ትቀባቸዋለህ፣ ትቀድሳቸው ማለህ፣ **ዘፀአ.** ፳፰፡፵፩ (ዘሌዋ. ፰፡፮–፲፪፣ ፴)። ለሕዝቤ ለእስራኤል አለቃ ይሆን ዘንድ ትቀባዋለህ፣ ፩ ሳሙ. ፱፡፲፮፣ ፲፡፩።

ሽማግሌዎች የታመመውን ዘይት ቀብተው ይጸ ልዩለት፣ ያዕ. ፭፡፲፬–፲፭ (ት. እና ቃ. ፵፪፡፵፩)።

መቀየር፣ የተቀየረ። ደግምም ደቀ መዛሙርት፣ ዳግመኛ መወለድን፣ ከእግዚአብሔር መወለድ ተመልከቱ

እምነትን፣ ልብን፣ እና ህይወትን የእግዚአብ ሔር ፍላጎትን ለመቀበል እና ለመከተል መቀየር (የሐዋ. ፫፡፲፱)።

ቅያሬ ግለሰብ አስቀድሞ የሚያደርጉትን ለማ ቆምና የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ለመሆን ለመ ቀየር ውሳኔ ማድረግ ነው። ንስሀ መግባት፣ ለኃ ጢያት ስርየት መጠመቅ፣ እጆችን በመጫን መን ፈስ ቅዱስን መቀበል፣ እና በጌታ ኢየሱስ ክርስ ቶስ እምነት መቀጥል ቅያሬን ተፈጻሚ ያደርጋል። ፍጥረታዊ ሰው የተቀደሰና ንጹህ፣ እንደገና በኢየ ሱስ ክርስቶስ የተወለደ በመሆን ለመቀየር ይችላል (፪ ቆሮ. ፭፡፲፯፣ ሞዛያ ፫፡፲፱)።

ሰዎች መቀየር እና እንደ ትንሽ ልጆች መሆን አለባቸው፣ **ማቴ.** ፲፰፡፲ (ሞዛያ ፫፡፲፱)። አን

ተም በተመለከህ ጊዜ ወንድሞችህን አጽና፣ ሉቃ. ፳፪፡፡፴፪። ቃሉን በደስታ የተቀበሉት ተጠመቁ፣ **የሐዋ.** ፪፡፡፴፯–፴፭። ኃጢአተኛን ከተሳሳተበት መንገድ መልስ፣ ያዕ. ፭፡፡፳።

ኢኖስ ተቀየረ፣ **ኢኖስ** ፭፡፡፪–፭። የንጉስ ቢን ያም ቃላት ታላቅ ለውጥ ለህዝቦች አመጣ፣ **ሞዛያ** ፭፡፡፪ (አልማ ፭፡፡፲፪–፲፱)። የሰው ዘር ሁሉ እንደገና መወለድ፣ አዎን በእግዚአብሔር መወለድ፣ አለ በት፣ **ሞዛያ** ፳፯፡፡፳፭። አልማ እና የሞስያ ልጆች ተቀየሩ፣ **ሞዛያ** ፳፯፡፡፴፣–፴፭። የላሞኒ አባት ተቀ የረ፣ **አልማ** ፳፪፡፡፲፭–፲፳። በእግዚአብሔር ሀይ ልና ቃል፣ ወደ ጌታ ተቀየሩ፣ **አልማ** ፴፣፡፡፲። ንስሀ መግባት የልብ ቅያሬን ያመጣል፣ **ሔሌ.** ፲፭፡፡፯። ብዙዎች በሚያምኑበት በኢየሱስ ክርስቶስ በነበ ረው የእግዚአብሔር ኃይል እና መንፈስ እንዲሁም ሥልጣን እንደተነበዮ በእውነት ለህዝቡ አስታው ቀዋል፣ ፫ ኔፊ ፯፡፡፳፭። በእኔ በነበራቸው እምነት የተነሳ በእሳት እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስ ተጠ መቁ፣ ፫ ኔፊ ፱፡፡፳።

ይሂዱ፣ እና ለህዝቦቹም ንስሀ መግባትን ይስበኩ፣ ት. እና ቃ. ፴፱፡፡፣–፴።

መቀደስ፣ የቅድስና ህግ። ደግምም የትብብር ስርዓት፤ የእግዚአብሔር መንግስት ወይም መንግስተ ሰማያት ተመልከቱ

መቀደስ፣ ቅዱስ ማድረግ፣ ወይም ጻድቅ መሆን። የቅድስና ህግ ወንዶች እና ሴቶች ጊዜአ ቸው፣ ችሎታቸውን፣ እና የንብረት ሀብታቸውን የእግዚአብሔር መንግስትን ለመመስረትና ለመገ ንባት በምርጫ የሚቀድሱበት መለኮታዊ መመ ሪያ ነው።

ዛሬ እጃችሁን ለእግዚአብሔር ቅዱስ አድርጉ፣ **ዘፀአ.** ፴፪፡፡፳፱።

የሚያምኑት ሁሉ ያላቸውንም ሁሉ በአንድነት ያዙ፣ **የሐዋ.** ፪፡፡፴፬–፴፭።

ሁሉም ነገሮች በጋራ ነበሩአቸው፣ ስለዚህ ድሃና ሃብታም አልነበራቸውም፣ ፬ ኔፊ ፩፡፡፣።

ጌታ የቅድስና መሰረታዊ መመሪያን ገለጸ፣ ት. እና ቃ. ፵፪፡፡፴–፴፱ (ት. እና ቃ. ፶፩፡፡፪–፣፱፣ ፶፯፡፡፴፭–፴፯)። አንድ ሰው ከሌላ በላይ ንብረት አይኑረው፣ ት. እና ቃ. ፵፱፡፡፳። እያንዳንዱ ሰው በቤተሰቡ መሰረት በድርሻው እኩል ይሰጠው፣ ት. እና ቃ. ፶፭፡፡፣። ቅዱሳን በሰማያዊና በምድራዊ ነገሮች በእኩል እንዲተሳሰሩ ዘንድ ስነስርዓት ተመ ስርቶ ነበር፣ ት. እና ቃ. ፫፯፡፡፬–፭። እያንዳንዱ ሰው በሚፈልገውና በሚያስፈልገው መሰረት እኩል ይገባኛል አለው፣ ት. እና ቃ. ፲፪፡፡፣–፲፱። ፅዮን በሰለስቲያል ህግ መሰረታዊ መርሆች ብቻ መገን ባት ትችላለች፣ ት. እና ቃ. ፲፭፡፡፭።

፲፯ የሌኖክ ህዝቦች የአንድ ልብ እና የአንድ አእ ምሮ ስለነበሩ፣ እና በጽድቅ ስለኖሩ፣ እና በመካከ ላቸውም ማንም ድሀ አልነበረም፣ **ሙሴ** ፣፡፡፲፯።

መቃብር። ደግምም ትንሳኤ ተመልከቱ

የምድራዊ ሰውነት መቀበሪያ ቦታ። በኃጢያት ክፍያ ምክንያት፣ እያንዳንዱ ሰው ከመቃብር በት ንሳኤ ይነሳል።

ክርስቶስ ከሞት ከተነሳ በኋላ፣ መቃብሮች ተከ ፈቱ እና ብዙ ሰውነቶች ተነሱ፣ **ማቴ.** ፳፯፡፡፶፪–፶፫ (፫ ኔፊ ፳፫፡፡፱–፣፫)። ሲኦል ሆይ፣ ድል መንሣትህ የት አለ፣ ፩ ቆሮ. ፣፭፡፡፶፭።

መቃብርም የያዘቻቸውን አካላት ማስረከብ አለ ባት፣ ፪ ኔፊ ፱፡፡፣፭–፣፫።

በመቃብራቸው የሚያነቀላፉትም ይመጣሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፫፡፡፣–፣፯። የማጥመቂያም ገንዳ የመቃብር ምሳሌ ነው፣ ት. እና ቃ. ፲፳፡፡፣–፣፫።

መቆጠር። ደግምም ማክበር፤ ክብር ተመልከቱ

ሰውን ወይም አንድ ነገርን፣ በተለይ በወንጌል አስተያየት፣ ብቁነት እና ዋጋ እንዳለው መመል ከት።

ከሰውም የተጠላ ነው፣ እኛም አላከበርነውም፣ **ኢሳ.** ፶፣፡፡፣–፬።

በሰው ዘንድ የከበረ በእግዚአብሔር ፊት ርኵሰት ነው፣ **ሉቃ.** ፣፣፯፡፡፣፭። እያንዳንዱ ባልን ጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቀሥ ጠር፣ **ፊልጵ.** ፪፡፡፫።

ጌታ ሁሉንም ሕዝብ በአንድ ዐይን ይመለከታል፣ ፩ ኔፊ ፣፯፡፡፴፭። እያንዳንዱ ሰው ጎረቤቱን እን ደራሱ ያክብር ዘንድ ጥብቅ ትዕዛዝ ነበር፣ **ሞዛያ** ፳፯፡፡፬ (ት. እና ቃ. ፴፯፡፡፳፯–፳፭)።

በሰላም ቀናቸው ምክሬን ትንሽ ዋጋ እንዳለው ተመለከቱት፣ ት. እና ቃ. ፣፭፡፡፳።

መበለት። ባል የሞተባት *ተመልከቱ*

መበርታት፣ ብርቱነት። ደግምም እምነት፣ *ማመን፤ ፍርሀት ተመልከቱ*

በልዩም ትክክለኛውን ለማድረግ አለመፍራት።

ጽኑ፡ አይዞአችሁ፣ **ዘዳግ.** ፴፩፡፡፣ (ኢ.ያ. ፩፡፡፣–፣)። የተጻፈውን ሁሉ ለመጠበቅና ለማድረግ በጣም በርቱ፣ **ኢ.ያ.** ፳፣፡፡፣።

እግዚአብሔር የፍርሃት መንፈስ አልሰጠንም፣ ፪ ጢሞ. ፩፡፡፣።

ይህን ሲሰማ ልቡ በረታ፣ **አልማ** ፣፭፡፡፬ (አልማ ፳፪፡፡፩)። የሔለማን ልጆች በድፍረትም ጀግኖች ነበሩ፣ **አልማ** ፴፣፡፡፳–፳፩። እንዲህ ያለን ታላቅ ድፍረትን በጭራሽ አላየሁም፣ **አልማ** ፴፣፡፡፴፭።

በርቱ፣ ወንድሞች፣ እና ወደ ድል ሂዱ፣ ት. እና ቃ. ፲፳፡፡፳፪።

መበተን። እስራኤል—የተበተኑት እስራኤል *ተመልከቱ*

መበደል

መለኮታዊ ህግን መተላለፍ፣ ኃጢያት መስራት፣ ወይም ችግር ወይም ጉዳት እንዲገኝ ማድረግ ነው፤ ደግሞም ማስከፋት ወይም ማናደድ ነው።

የተበደለ ወንድም እንደ ጸናች ከተማ ጽኑ ነው፣ ምሳ. ፲፰፡፲፱።

ቀኝ ዓይንህም ብታሰናክልህ አውጥተህ ከአንተ ጣላት፣ ማቴ. ፭፡፳፱። ከእነዚህ ከታናናሾቹ አን ዱን የሚያሰናክል ሁሉ፥ የወፍጮ ድንጋይ በአ ንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቅ ባሕር መስጠም ይሻለው ነበር፣ ማቴ. ፲፰፡፮ (ት. እና ቃ. ፱፳፭፡፲፱–፳፪)።

ወንድሞቻችሁ ወይም እህቶቻችሁ ቢያስቀይሟ ችሁ፣ ከተናገዘ ወይም ከተናገዘችም ትታረቃላ ችሁ፣ ት. እና ቃ. ፵፪፡፹፰። የእርሱ እጅ እን ዳለበት ከማይመሰክሩ እና ትእዛዙን ከማያከብሩ በቀር፣ በምንም ሰው እግዚአብሔርን አያስቀይመ ውም፣ ወይም በማንም ላይ ቁጣው አይቀጣጠልም፣ ት. እና ቃ. ፹፱፡፳፭።

መባህ። በኩራት *ተመልከቱ*

መባረክ፣ የተባረከ፣ በረከት። *ደግምም ህግ፣ ለታመሙት አገልግሎት መስጠት፣ አመስጋኝ፣ ምስጋናን፣ ምስጋና መስጠት፣ የፓትሪያርክ በረከቶች፣ ጸጋ ተመልከቱ*

መለኮታዊ ድጋፍን ለአንድ ሰው መስጠት። ለእውነተኛ ደስታ፣ ለደህንነት፣ ወይም ለብል ፅግና ተጨማሪ ምክንያት የሚሆነው ማንኛውም ነገር በረከት ነው።

በረከቶች ሁሉ በዘለአለማዊ ህግጋት ላይ የተመ ሰረቱ ናቸው (ት. እና ቃ. ፲፬፡፳–፳፩)። እግዚአ ብሔር ልጆቹ በእዚህ ህይወት ደስታን እንዲያገኙ እልስሚፈልግ (፪ ኔፊ ፪፡፳፭)፣ ለትእዛዛቱ ታዛ ዥነታቸው ውጤታ (ት. እና ቃ. ፹፪፡፲)፣ ለጸ ሎት መልስ ወይም ለክህነት ስልጣን ስነስርዓት (ት. እና ቃ. ፲፱፡፴፯፣ ፲፯፡፳፭–፳፯)፣ ወይም በጸጋው በኩል (፪ ኔፊ ፳፭፡፳፫) በረከቶችን ይሰ ጣቸዋል።

ክርስቶስ ስለመባረክ የተናገራቸው አረፍት ነገ ሮች ታዋቂ የሆኑ ስለብሩክነት መግለጫ የተዘረዘረ ነው (ማቴ. ፭፡፩–፲፪፣ ፫ ኔፊ ፲፪፡፩–፲፪)።

አጠቃላይ፣ ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ፣ እባ ርክሃለሁ፣ ዘፍጥ. ፲፪፡፪–፫ (፩ ኔፊ ፲፭፡፲፰፣ አብር. ፪፡፱–፲፩)። በረከት በጻድቅ ራስ ላይ ነው፣ ምሳ. ፲፡፮። የታመነ ሰው እጅግ ይባረካል፣ ምሳ. ፳፰፡፳። ጌታ የሰማይ መስኮትን ይከፍታል እና በረ ከቶችን ያፈስልሀል፣ ሚል. ፫፡፣ ፲ (፫ ኔፊ ፳፬፡፣)።

ክርስቶስ ስለተባረኩ የተናገራቸው አረፍት ነገ ሮች የበረከቶች የተስፋ ቃል ይሰጣሉ፣ ማቴ. ፭፡፩–፲፪ (፫ ኔፊ ፲፪፡፩–፲፪)። ወደ በጉ ሰርግ እራት የተ ጠሩ ብፁዓን ናቸው፣ ራዕ. ፲፱፡፱።

ጻድቅ የሆነ በእግዚአብሔር የተወደደ ነው፣ ፩ ኔፊ ፲፯፡፴፩ (ሞዛያ ፲፡፲፫)። ካዳመጣችሁ፣ በረከት እተውላችኋለሁ፣ ፪ ኔፊ ፩፡፳፰። ለእና ንተ አንድ አይነት በረከት እተውላችኋላሁ፣ ፪ ኔፊ ፱፡፱። ወዲያው ባረካችሁ፣ ሞዛያ ፪፡፳፩። በእርሱ ላይ እምነታቸውን ለሚያሳርፉ ጌታ ባረካቸውም አበለጸጋቸውም፣ ሔሌ. ፲፪፡፩።

ስራዬን ለማምጣት እርዳታ ስጥ፣ እናም ትባረካ ለህ፣ ት. እና ቃ. ፮፡፱። ሁልጊዜም ጸልይ፣ እናም በረከትህ ታላቅ ይሆናል፣ ት. እና ቃ. ፲፱፡፴፰። ተጠመቅ፣ እናም መንፈሴን እንዲሁም ከምታ ውቀው በላይ ታላቅ የሆነን በረከት ትቀበላለህ፣ ት. እና ቃ. ፴፱፡፲። ከብዙ ፈተናዎች በኋላ በረከ ቶች መጡ፣ ት. እና ቃ. ፹፰፡፱። ሰዎች ትእዛዛትን አያከብሩም፣ እመነጥቃለሁ እና በረከቶችን አይ ቀበሉም፣ ት. እና ቃ. ፹፰፡፴፱። አብ ያዘጋጀላ ችሁ በረከት እንዴት ታላቅ እንደሆነ አልገባችሁም፣ ት. እና ቃ. ፷፰፡፲፯። በሊቀ ካህናት በኩል በቤተክ ርስትያኗ ላይ የስነስርዓቶች መከናወን እና በረከቶች መጡ፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፴፭–፴፮። ሁሉም በረከ ቶች የሚሞረከዙበት ህግ አለ፣ ት. እና ቃ. ፲፴፡፳። በእጆቹ በረከቶችን የሚያገኙ በህግጋቱ ይኖራሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፴፪፡፭። በረከቶች ጌታን ለሚወዱት ተጠብቀው ተይዘዋል፣ ት. እና ቃ. ፲፴፯፡፹፪።

አብርሐም የአባቶችን በረከቶችና እነዚህን የማ ስተዳደር መብት ፈለገ፣ አብር. ፩፡፪።

ልጆችን መባረክ፣ አቀፋቸውም እጁንም ጭኖ ባረካቸው፣ ማር. ፣ ፲፮።

ህጻናቶቻቸውን አንድ በአንድ ወሰደ፣ እናም ባረ ካቸው፣ ፫ ኔፊ ፲፯፡፳፩።

ሽማግሌዎች ልጆችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይባርኩ፣ ት. እና ቃ. ፳፡፷።

መብት። *ደግምም* ባርነት፣ ነጻ ምርጫ፣ ነጻ፣ *ነጻነት ተመልከቱ*

በነጻነት ለመስራት እና ለማሰብ የሚኖር ችሎታ። በወንጌል መሰረታዊ መርሆች ታዛዥ መሆን ከኃጢ ያት መንፈሳዊ ባርነት ሰውን ነጻ ያደርጋል (ዮሐ. ፰፡፴፩–፴፮)።

ትእዛዛትህንም ፈልጌአለሁና አስፍቼ እሄዳለሁ፣ መዝ. ፻፲፱፡፴፭።

የጌታም መንፈስ ባለበት በዚያ አርነት አለ፣ ፪ ቆሮ. ፫፡፣ ፲፯። ጸንታችሁ ቁሙ እንደ ገናም በባ ርነት ቀንበር አትያዙ፣ ገላ. ፭፡፩ (ት. እና ቃ. ፹፰፡፹፱)።

ሰዎች ነፃነትን ወይም ዘለዓለማዊ ህይወትን ለመ ምረጥ ነፃ ናቸው፣ ፪ ኔፊ ፪፡፳፯። ይህ ምድር የነ

ፃነት ምድር ይሆናል፣ ፪ ኔፊ ፲፥፲፩። ሞሮኒ በኔፋውያን መካከል የነፃነት ዓርማው እንዲሰቀል አደረገ፣ አልማ ፵፮፥፴፮።

ጌታ እና አገልጋዮቹ ለታሰሩት ነጻነትን አወጁ፣ ት. እና ቃ. ፻፴፰፥፲፰፣ ፴፩፣ ፵፪።

መተርጎም

በአንድ ቋንቋ የተሰጠውን ትርጉም እና ሀሳብ በሌላ ቋንቋ በእኩል ሁኔታ መግለፅ (ሞዛያ ፰፥፰–፲፫፤ እ.አ. ፩፥፰)። በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ፣ ይህም እንደ እግዚአብሔር ስጦታ ይጠቀማል (አልማ ፱፥፳፩፤ ት. እና ቃ. ፰፤ ፱፥፯–፱)። አንዳንዴም ይህ በቋንቋ የተተረጎመውን ማሻሻል ወይም ማስተካከል ማለትም ወይም የጠፉትን ቃላት በዳግም መመለስም ሊሆን ይችላል (ት. እና ቃ. ፵፫፥፰–፳፩)። ጆሴፍ ስሚዝ የንጉስ ጄምስ መፅሐፍ ቅዱስን በመነሳሳት እንዲተረጉም ታዝዞ ነበር (ት. እና ቃ. ፵፪፥፶፮፤ ፸፮፥፲፭)።

ጆሴፍ ስሚዝ በእግዚአብሔር ምህረት፣ በእግዚአብሔር ኃይል መጽሐፈ ሞርሞንን የመተርጎም ኃይል ነበረው፣ ት. እና ቃ. ፩፥፳፱። የመተርጎም ስጦታ አለህ፣ ት. እና ቃ. ፭፥፬። ከእኔ የምትፈልግ ከሆነ እንድትተረጉም ስጦታን እሰጥሃለሁ፣ ት. እና ቃ. ፮፥፳፭። እግዚአብሔር ለጆሴፍ ስሚዝ መፅሐፈ ሞርሞንን ለመተርጎም ከላይ ሀይልን ሰጠው፣ ት. እና ቃ. ፳፥፰።

በኡሪምና ቱሚም ጥቅም አንዳንዶቹን ፊደኖች ተረጎመ፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፷፪ (ሞዛያ ፰፥፲፫፣ ፳፰፥፲፫)።

መተኛት

ሰው የማይንቀሳቀስ ወይም ሩሁን የሳተበት የእረፍት ሁኔታ። ጌታ ቅዱሳኑን ከሚያስፈልጋቸው በላይ እንዳይተኙ መከሯል (ት. እና ቃ. ፹፰፥፻፳፬)። መተኛት የመንፈስ ሞት (፩ ቆሮ. ፲፩፥፴፤ ፪ ኔፊ ፩፥፲፫) ወይም የስጋዊ ሞት (ሞር. ፱፥፲፫) ምልክትም ሊሆን ይችላል።

መታመን። ደግሞም ልበ ሙሉነት፤ እምነት፤ ማመን ተመልከቱ

በአንድ ሰው ወይም በአንድ ነገር ላይ መመካት ወይም እምነትን መጣል። በመንፈሳዊ ነገሮች፣ ማመን በእግዚአብሔር እና በመንፈሱ መመካት ነው።

ቢገድለኝ ስንኳ እርሱን በትዕግሥት እጠባበቃለሁ፣ ኢዮብ ፲፫፥፲፭። በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፣ ምሳ. ፫፥፭። እግዚአብሔር በእርሱ የሚያምኑትን አገልጋዮች አዳነ፣ ዳን. ፫፥፲፱–፳፰።

ለዘለዓለም በአንተ እታመናለሁ፣ ፪ ኔፊ ፬፥፴፬። ተደሰቱ፣ እናም በእግዚአብሔር እምነታችሁን አድርጉ፣ ሞዛያ ፯፥፲፱። እምነቱን በእርሱ ያደረገ በመጨረሻው ቀን ከፍ ይላል፣ ሞዛያ ፳፫፥፳፪። እምነታቸውን በእግዚአብሔር ላይ ያደረጉ ሁሉ፣ በፈተናቸውይደገፋሉ፣ አልማ ፴፮፥፫፣ ፳፯።

በስጋ ክንድ አትመካ፣ ት. እና ቃ. ፩፥፲፱። ወደ መልካም በሚመራው መንፈስ ላይ እምነትህን አድርግ፣ ት. እና ቃ. ፲፩፥፲፪። በእኔ ይመን እናም ግራ አይጋባ፣ ት. እና ቃ. ፹፬፥፻፲፮።

መኃልይ መኃልይ ዘሰለሞን

የብሉይ ኪዳን መፅሀፍ። ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ መኃልይ መኃልይ ዘሰለሞን የተነሳሳ ጽሁፍ አይደለም ብሎ አስተምሯል።

መነሳሳት። ህያው ማድረግ ተመልከቱ

መነሳሻ፣ መነሳሳት። ደግሞም መንፈስ ቅዱስ፤ ራዕይ ተመልከቱ

ለሰው በእግዚአብሔር የተሰጠው መኮታዊ አመራር። መነሳሳት ከመንፈስ የሚመጣው በተለያዩ መንገዶች ወደ ሰው አዕምሮና ልብ ነው።

ከእሳቱም በኋላ ትንሽ የዝምታ ድምፅ ሆነ፣ ፩ ነገሥ. ፲፱፥፲፪።

መንፈስ ቅዱስ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል፣ ዮሐ. ፲፬፥፳፮። የእውነት መንፈስ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፣ ዮሐ. ፲፮፥፲፫።

ማድረግ ያለብኝን ነገሮች ቀድሜ ሳላውቅ በመንፈስ ተመራሁ፣ ፩ ኔፊ ፬፥፮። የጌታ ድምፅ በአዕምሮዬ መጣ፣ ኢኖስ ፩፥፲። ያለማቋረጥ መልካምን እንዲሰሩ የሚጋብዝ እናም የሚገፋፉ በእግዚአብሔር የሚነሳሳ ነው፣ ሞሮኒ ፯፥፲፫–፲፮።

በአምሮህ ሰላምን አልተናገርኩህምን፣ ት. እና ቃ. ፮፥፳፫። በአዕምሮህ እና በልብህ እነግርሃለሁ፣ ት. እና ቃ. ፰፥፪። መንፈሴ አእምሮህን ያብራራል፣ ነፍስህን በደስታ ይሞላል፣ ት. እና ቃ. ፲፩፥፲፫። በዛኑ ግዜ የምትናገርውን እና የምትጽፈውን ይሰጥሃል፣ ት. እና ቃ. ፳፬፥፮ (ት. እና ቃ. ፹፬፥፹፭)። ትንሽ የዝምታ ለስላሳ ድምፅም በሁሉም ነገሮች አሾከሸከ እና ሰንጥቆ ገባ፣ ት. እና ቃ. ፹፭፥፮።

መና። ደግሞም ኦሪት ዘፀአት፤ የህይወት እንጀራ ተመልከቱ

የማር ጣም ያለው ትንሽ፣ ክብ የመሰለ ምግብ (ዘፀአ. ፲፮፥፲፬–፴፩) ወይም አዲስ ዘይት (ዘኍል. ፲፩፥፯–፰)። በምድረበዳ ውስጥ በነበሩበት በአርባ አመታት ጊዜ ጌታ የእስራኤል ልጆችን ለመመገብ ይህን ሰጣቸው (ዘፀአ. ፲፮፥፬–፭፣ ፲፬–፴፣ ፴፭፤ ኢያ. ፭፥፲፪፤ ፩ ኔፊ ፲፯፥፳፰)።

የእስራኤል ልጆች መና (ወይም በዕብራውያን

ቋንቋ ማን-ሁ) ብለው ጠሩት—ይህም “ምንድን ነው?” ማለት ነው—ምክያቱም ምን እንደሆነ አላ ወቁምና (ዘፀአ. ፲፮፡፲፭)። ደግሞም ይህ “የመላእ ክት ምግብ” እና “የሰማይ እንጀራ” ተብሎ ይታወ ቃል (መዝ. ፹፰፡፳፡፳፭፣ ዮሐ. ፮፡፴፩)። ይህም የህይወት እንጀራ የሚሆነው የክርስቶስ ምሳሌ ነበር (ዮሐ. ፮፡፴፩–፴፭)።

መናቅ። መጥላት፣ ጥላቻ *ተመልከቱ*

መናዘዝ። *ደግሞም መጸጸት፣ ንስሀ መግባት፣ ይቅርታ ማድረግ ተመልከቱ*

ቅዱሳት መጻህፍት *መናዘዝን* በሁለት መንገዶች ተጠቅመውበታል። በሌላ አባባል፣ መናዘዝ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ መናዘዝ አይነት በአንድ ነገር የእራስን እምነት ሁኔታ መግለፅ ነው (ማቴ. ፲፡፴፪፣ ሮሜ ፲፡፱፣ ፩ ዮሐ. ፬፡፩–፫፣ ት. እና ቃ. ፲፲፡፲፡፲፬)።

መናዘዝ፣ እንደ ኃጢያት መናዘዝ አይነት፣ ለራስ ወንጀለኛነት ተቀባይ መሆን ማለት ነው። ሁሉም ሰው ኃጢያቶቻቸውን ሁሉ ለጌታ መናዘዝ እና የእርሱን ምህረት የማግኘት ሀላፊነት አላቸው (ት. እና ቃ. ፶፮፡፶፪–፶፫)። አስፈላጊም ሲሆን፣ ኃጢያቶች ለተሰራበት ወይም ለተሰራባቸው ሰዎች መናዘዝ ያስፈልጋል። ሀይለኛ ኃጢያቶች ለቤተክር ስቲያኗ ባለስልጣናት (በብዙም ጊዜ ለኤጲስ ቆጶስ) መናዘዝ ይገባል።

የሠራውን ኃጢአት ይናዘዛል፣ **ዘሌዋ.** ፭፡፭። ኃጢአታቸውንም ይናዘዛሉ፣ **ዘሌዋ.** ፳፮፡፵–፵፪። ለእግዚአብሔር ክብር ስጥ፡ ለእርሱም ተናዘዝ፣ **ኢያ.** ፯፡፲፱። ሰዎች ኃጢአታቸውንም እየተናዘዙ በዮርዳኖስ ወንዝ ከእርሱ ይጠመቁ ነበር፣ **ማቴ.** ፫፡፭–፮። ኃጢያታቸውን የተናዘዙት ተላላፊዎች ይቅርታ ይሰጣቸዋል፣ **ሞዛያ** ፳፮፡፳፱። ኃጢያትህን ተናዘዝ አለበለዚያም ቅጣቶችን ትሰ ቃያለህ፣ **ት. እና ቃ.** ፲፱፡፳። ንስሀ የሚገቡ ኃጢ ያቶቻቸውን ይናዘዛሉ እናም ይተዉአቸዋልም፣ **ት. እና ቃ.** ፶፮፡፶፫። ጌታ ኃጢያቶችን በትሁት ልብ ለሚናዘዙት መሀሪ ነው፣ **ት. እና ቃ.** ፳፭፡፪። ጌታ ለሚናዘዙና ይቅርታን ለሚጠይቁ ኃጢያቶችን ይቅርታ ያደርጋል፣ **ት. እና ቃ.** ፳፬፡፲። ፡

መንገድ። *ደግሞም መራመድ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መራመድ (መሄድ)፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልከቱ*

ሰው የሚከተለው መንገድ ወይም አቅጣጫ። ኢየሱስ መንገዱ ነኝ አለ (ዮሐ. ፲፬፡፩–፮)።

በመንገዱም እንድትሄድ የእግዚአብሔርን ትእ ዛዝ ጠብቅ፣ ዘዳግ. ፭፡፲። ልጅን በሚሄድበት መን ገድ ምራው፣ ምሳ. ፳፪፡፮ (፪ ኔፊ ፱፡፳)። መን ገዴ ከመንገዳችሁ ከፍ ያለ ነው፣ ኢሳ. ፶፭፡፰–፱። ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ፥ መን ገዱም የቀጠነ ነውና፣ **ማቴ.** ፯፡፲፫–፲፬ (፫ ኔፊ ፲፬፡፲፫–፲፭፣ ፳፯፡፲፣ ት. እና ቃ. ፲፭፡፳፪፡፳፭)። እግዚአብሔር ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል፣ ፩ ቆሮ. ፲፡፲፫።

ጌታ ያዘዛቸውን ትዕዛዛት የሚሟሉበትን መንገድ ካላዘጋጀ በቀር ለሰው ልጆች ትዕዛዛትን አይሰጥም፣ ፩ ኔፊ ፫፡፯ (፩ ኔፊ ፱፡፯፣ ፲፯፡፣ ፲፫)። በመግቢ ያው ካልሆነ በቀር ምንም ሌላ መንገድ የለም፣ ፪ ኔፊ ፱፡፶፩። በራሳችሁ ዘለዓለማዊውን ሞት ወይም የዘ ለዓለማዊውን ህይወት መንገድ እራሳችሁ ለመም ረጥ ነጻነት አላችሁ፣ ፪ ኔፊ ፲፡፳፫። መንገዱ ይህ ነው፤ የተሰጠ ሌላ መንገድም ሆነ ስም የለምና፣ ፪ ኔፊ ፴፩፡፳፩ (ሞዛያ ፫፡፲፯፣ አልማ ፴፯፡፱፣ ሔለ. ፭፡፱)። እግዚአብሔርም በልጁ ስጦታም ይበ ልጥ የተመረጠውን መንገድ አዘጋጅቷል፣ **ኤተር** ፲፪፡፲፩ (፩ ቆሮ. ፲፪፡፴፩)።

ሁልም ሰው በራሱ መንገድ ይጓዛል፣ **ት. እና ቃ.** ፩፡፲፮። ይህም በእኔ መንገድ መደረግ አለበት፣ **ት. እና ቃ.** ፲፱፡፲፮።

መንግስት። *ደግሞም ህገ መንግስት ተመልከቱ*

ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመለስ፣ የጻድቅ መንግስት ይመሰርታል።

አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፣ **ኢሳ.** ፱፡፮ (፪ ኔፊ ፲፱፡፮)።

እንኪያስ የቄሣርን ለቄሣር አስረክቡ፣ **ማቴ.** ፳፪፡፳፩ (ት. እና ቃ. ፳፫፡፳፮)። ለባለ ሥልጣ ኖች ይገዛ፣ **ሮሜ** ፲፫፡፩ ለነገሥታትና ለመኳን ንትም ሁሉ ጸልይ፣ ፩ ጢሞ. ፪፡፩–፪ ለገዦችና ለባለ ሥልጣኖች የሚገዙና የሚታዘዙ ሁኑ፣ ቲቶ ፫፡፩ ስለ ጌታ ብላችሁ ለሰው ሥርዓት ሁሉ ተገዙ፣ ፩ ጴጥ. ፪፡፲፫–፲፰ የዓለም መንግሥት የክርስቶስ ትሆናለች፣ ራዕ. ፲፩፡፲፭።

ፃድቅ ሰው የእናንተ ንጉስ ይሁን፣ ሞዛያ ፳፫፡፳ በህዝቡም ድምፅ ጉዳያቸሁን ፈፅሙ፣ ሞዛያ ፳፱፡፳፯።

ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ የእኛ ገዢ ይሆናል፣ **ት. እና ቃ.** ፴፩፡፱። የእግዚአብሔርን ህግጋትን የሚጠብቅ የምድርን ህግጋት የመጣስ ፍላጎት አይ ኖረውም፣ **ት. እና ቃ.** ፶፮፡፳፩። ክፉው ሲያስተ ዳድር ህዝቡ ያዝናል፣ **ት. እና ቃ.** ፶፮፡፱–፲። መን ግስቶች እግዚአብሔር ለሰው ጥቅም የመሰረታቸው ናቸው፣ **ት. እና ቃ.** ፲፴፬፡፩–፭። ሰዎች መንግ ስቶች ለመቀበል እና ለመደገፍ ግዴታ አላቸው፣ **ት. እና ቃ.** ፲፴፬፡፭።

፲፪ ለንጉሶች፣ ለፕሬዘደንቶች፣ ለመሪዎች፣ እናም ለዳኛዎች ታዛዦች በመሆን፣ በህግ በመ

ታዘዝ፣ በማክበርና በመደገፍ እናምናለን፣ እ.አ. ፩፡፲፪።

መንፈሳዊ ሞት። ደግሞም ሲያል፤ ኩነኔ፤ የአዳም እና የሔዋን ውድቀት፤ የጥፋት ልጆች፤ ደህንነት፤ ዲያብሎስ ተመልከቱ

ከእግዚአብሔር እና ከተፅዕኖው መለየት፤ ጻድቅን ከሚነኩ ነገሮች መሞት። ሉሲፈር እና ከሰማይ ሰራዊት አንድ ሶስተኛቹ ከሰማይ በሚወረወሩበት ጊዜ በመንፈስ ሞቱ (ት. እና ቃ. ፹፱፡-፹፯)።

መንፈሳዊ ሞት ወደ አለም የተዋወቀው በአዳም ውድቀት ምክንያት ነው (ሙሴ ፮፡፶፯)። ክፉ ሀሳቦች፣ ቃላት፣ እና ስራዎች ያላቸው ስጋዊ ሰዎች በምድር ላይ በህይወት እያሉ በመንፈስ የሞቱ ናቸው(፩ ጢሞ. ፭፡፮)። በኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢያት ክፍያ በኩል እና ለወንጌሉ መሰረታዊ መርሆችና ስነስርዓቶች ታዛዥ በመሆን፣ ወንዶች እና ሴቶች ከኃጢያት ንጹህ ለመሆንና መንፈሳዊ ሞትን ለማሸነፍ ይችላሉ።

መንፈሳዊ ሞት ደግሞም የስጋዊ ሰውነት ሞትን በመከተል ለደርስ ይችላል። ከሞት የተነሱ ሰዎች እና ዲያብሎስና መላእክቱ ይፈረድባቸዋል። በወንጌሉ ብርሀን እና እውነት ላይ በፈቃደኝነት የሚያምጹ በመንፈሳዊ ሞት ይሰቃያሉ። ይህ ሞት ብዙም ጊዜ ሁለተኛ ሞት ይባላል (አልማ ፲፪፡፲፯፤ ሔለ. ፲፩፡፲፯-፲፱፤ ት. እና ቃ. ፫፯፡፴፯-፴፰)።

ክፉ አድራጊዎች ይጠፋሉ፤ መዝ. ፴፯፡፱።

ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነው፣ ሮሜ ፰፡፮ (፪ ኔፊ ፱፡፴፱)። ምኞት ሰዎችን በፈተና እና በወጥመድም ያጠፋቸዋል፣ ፩ ጢሞ. ፮፡፱። ኃጢአት ሞትን ትወልዳለች፣ ያዕ. ፩፡፲፭። ድል የነሣው በሁለተኛው ሞት አይጐዳም፣ ራዕ. ፪፡፲፩። ሁለተኛው ሞት በእነርሱ ላይ ሥልጣን የለውም፣ ራዕ. ፳፡፮፣ ፲፪-፲፬። ኃጢያተኞች ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው፣ ይኸውም ሁለተኛው ሞት ነው፣ ራዕ. ፳፩፡፰ (ት. እና ቃ. ፹፫፡፲፮-፲፰)።

ሰዎች ነፃነትን ወይም ዘለዓለማዊ ህይወትን ለመምረጥ፣ ወይም እንደዲያብሎስ ምርኮና ሀይል ምርኮንና ሞትን ለመምረጥ ነፃ ናቸው፣ ፪ ኔፊ ፪፡፳፯ (፪ ኔፊ ፲፡፳፫፣ አልማ ፳፱፡፮፣ ሔለ. ፲፩፡፴-፴፩)። እግዚአብሔር ከሞትና ከሲኦል የምናመልጥበት መንገድ አዘጋጅቷል፣ ፪ ኔፊ ፱፡፲። እናም የዲያብሎስ መልዕክተኛ በመሆን የሁለተኛው ሞት ከሆነው እሳትና ዲን ራሳችሁን እንዳትጥሉ ከሲያል ህመም ራሳችሁን ፍቱ፣ ያዕቆ. ፫፡፲፩። ፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር ጠላት ነው፣ ሞዛያ ፫፡፲፱። በሁለተኛ ሞትም እንዳትሰቃዩ፣ ጌታ ንስሃን ይስጣችሁ፣ አልማ ፲፫፡፴። አልማ በዘለአለማዊው የሞት ሰንሰለት ተከብቦ ነበር፣ አልማ ፴፮፡፲፯። ኃጢያተኞች ጻድቅ ለሆኑት ነገሮች ይሞታሉ፣ አልማ ፴፡፳፯ (አልማ ፲፪፡፲፯)። ውድቀት በሰው ዘር በሙሉ የመንፈስ ሞትን አመጣ፣ አልማ ፴፪፡፱ (ሔለ. ፲፬፡፲፯-፲፰)።

አዳም ሲወድቅ፣ በመንፈስ ሟች ሆነ፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፴-፴፩፣ ፴፬።

መንፈሳዊ ስጦታ። ደግሞም ቤተመቅደስ፣ የጌታ ቤት ተመልከቱ

በአጠቃላይ አስተሳሰብ፣ የእግዚአብሔር ሀይል ስጦታ። ብቁ የቤተክርስቲያኗ አባላት ዘለአለማዊነትን ለማግኘት የሚያስፈልጋቸውን መመሪያና የቅዱስ ክህነት ቃል ኪዳኖች በሚሰጣቸው በቤተመቅደስ ስነስርዓቶች በኩል የሀይል ስጦታን ይቀበላሉ። መንፈሳዊ ስጦታ ስለደህናነት አላማ መመሪያንም ይጨምራል።

በእዚያም ከላይ የኃይል መንፈሳዊ ስጦታም ይሰጣችኋል፣ ት. እና ቃ. ፴፯፡፴፪፣ ፴፪ (ሉቃ. ፳፬፡፵፱፣ ት. እና ቃ. ፴፫፡፲፯)። ቤት ገንቡ፣ በዚህ ቤትም የመረጥኳቸውን ከላይ መንፈሳዊ ስጦታ ለመስጠት አቅጃለሁ፣ ት. እና ቃ. ፣፲፭፡፰። ታላቅ መንፈሳዊ ስጦታ እና በረከት አዘጋጅቻለሁ፣ ት. እና ቃ. ፣፲፭፡፲፪፣ ፲፰፣ ፴፫። አገልጋዮቼ በተቀበሉት መንፈሳዊ ስጦታ ምክንያት የብዙዎች ልብ በታላቅ ይደሰታሉ፣ ት. እና ቃ. ፣፲፣፡፱። ግርማ፣ ክብር፣ እና መንፈሳዊ ስጦታ፣ በቅዱስ ቤቴ ስነ ስርዓት የተሾሙ ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፣፲፳፱፡፴፱። በአብ እንደ አሮን የተጠሩ በክህነት ስልጣን ቁልፎች ይበለፅጋሉ፣ ት. እና ቃ. ፣፴፪፡፣፴፱።

መንፈሳዊ ጭለማ። ደግሞም ክፉ፣ ክፋት ተመልከቱ

ጥፋተኛነት ወይም ስለመንፈሳዊ ነገሮች አላዋቂነት።

ጨለማውን ብርሃን ብርሃኑንም ጨለማ ለሚያደርጉ፣ ኢሳ. ፭፡፳ (፪ ኔፊ ፲፭፡፳)። ጨለማ ምድርን ድቅድቅ ጨለማም አሕዛብን ይሸፍናል፣ ኢሳ. ፷፡፪።

ኢየሱስ ብርሃኑም በጨለማና ተቀምጠው ላሉት ያበራል፣ ሉቃ. ፩፡፷፱። ብርሃንም በጨለማ ይበራል፡ ጨለማም አላሸነፈውም፣ ዮሐ. ፩፡፭ (ት. እና ቃ. ፴፭፡፣)። እንግዲህ የጨለማውን ሥራ አውጥተን የብርሃንን ጋሻ ጦር እንልበስ፣ ሮሜ ፣፲፡፡፲፪። ፍሬም ከሌለው ከጨለማ ሥራ ጋር አትተባበሩ፣ ኤፌ. ፭፡፣-፲፩።

ስላልጠየቃችሁ፣ ወይም ስላላንኳኳችሁ ነው፣ ስለሆነም፣ ወደ ብርሃኑ አልመጣችሁም፣ ነገር ግን በጨለማው ትጠፋላችሁ፣ ፪ ኔፊ ፴፪፡፱። ሰይጣን የጨለማ ስራን ያሰራጫል፣ ሔለ. ፣፡፳-፴፩።

የጨለማ ሀይሎች በምድር ላይ ይሰራጫል፣ ት. እና ቃ. ፴፣፡፣ ፣፲፩-፲፪። አለም በሙሉ

በጨለማና በኃጢያት ስር ይቃሰታሉ፣ ት. እና ቃ. ፹፰፥፷፯–፷፰። ለክብሬ ዐይናችሁ ቀና ብትሆን፣ በእናንተም ምንም ጭለማ አይኖርም፣ ት. እና ቃ. ፺፫፥፴፯።

እንደዚህም የጭለማ ስራዎች በሰው ልጆች ሁሉ መካከል መሳካት ጀመረ፣ ሙሴ ፭፥፶፭።

መንፈስ። *ደግሞም* ሰው፣ ሰዎች፤ ስጋዊ ሞት፤ ትንሳኤ፤ ነፍስ *ተመልከቱ*

ከምድራዊ ውልደት በፊት የነበረው፣ በስጋዊ ሰውነት ውስጥ በምድራዊ ህይወት ጊዜ የሚኖር፣ እናም ከሞት በኋላም እስከ ትንሳኤ ድረስ ተለይቶ የሚኖረው የህያው ሰው ክፍል። ሁሉም ህያው ነገሮች፣ የሰው ዘር፣ እንስሳት፣ እና ተክል፣ በምድር ላይ ምንም አይነት ህይወት ከመኖሩ በፊት መንፈሶች ነበሩ (ዘፍጥ. ፪፥፬–፭፤ ሙሴ ፫፥፬–፯)። የመንፈስ ሰውነት ከስጋ ሰውነት ጋር አንድ ይመስላሉ (፩ ኔፊ ፲፩፥፲፩፤ ኤተር ፫፥፲፭–፲፮፤ ት. እና ቃ. ፸፯፥፪፤ ፻፴፱)። መንፈስ ንጥረ ነገር ነው፣ ነገር ግን ከምንም ንጥረ ነገር በላይ የጠራ እና ንጹህ ነው (ት. እና ቃ. ፻፴፩፥፯)።

በምድር ላይ ወደ ሟች ወላጆች ከመወለዳቸው በፊት ለሰማይ ወላጆች እንደ መንፈስ የተወለደው እያንዳንዱ ሰው የእግዚአብሔር ወንድ ወይም ልጅ ነው (ዕብ. ፲፪፥፱)። በምድር ላይ ያለ እያንዳንዱ ሰው ከስጋ እና አጥንት ሰውነት በተጨማሪ የማይሞት የመንፈስ ሰውነት አለው። በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ አንዳንዴ ትርጉም እንደሚሰጣቸው፣ መንፈስ እና ስጋዊ ሰውነት በአንድነት ነፍስን ይሰራሉ (ዘፍጥ. ፪፥፯፤ ት. እና ቃ. ፹፰፥፲፭፤ ሙሴ ፫፥፯፣ ፱፣ ፲፱፤ አብር. ፭፥፯)። መንፈስ ያለስጋዊ ሰውነት ለመኖር ይችላል፣ ነገር ግን ስጋዊ ሰውነት ያለመንፈስ ለመኖር አይችልም (ያዕ. ፪፥፳፮)። ስጋዊ ሞት የመንፈስ ከሰውነት መለየት ነው። በትንሳኤ ጊዜ፣ ከሁለት ታላቅ ልዩ ጋር፣ መንፈስ በሟችነት እንደነበረው ምድራዊ የስጋ እና የአጥንት ሰውነት ጋር እንደገና አንድ ይሆናል፥ ሁለቱም እንደገና አይለያዩም፣ እና ስጋዊ ሰውነት ዘለአለማዊ እና ፍጹም ይሆናል (አልማ ፲፩፥፵፭፤ ት. እና ቃ. ፻፴፰፥፲፮–፲፯)።

በእኔ እንደምታዩት፥ መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውም፣ ሉቃ. ፳፬፥፴፱። የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል፣ ሮሜ ፰፥፲፮። በሥጋችሁ፣ እናም በመንፈሳችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ፣ ፩ ቆሮ. ፮፥፳።

ይህ ሰውነት መንፈሳዊው ሰውነቴ ነው፣ ኤተር ፫፥፲፮።

ሰው መንፈስ ነው፣ ት. እና ቃ. ፺፫፥፴፫። ክርስቶስ ለጻድቃን መንፈሶች በገነት አስተማረ፣ ት. እና ቃ. ፻፴፰፥፳፰–፴ (፩ ጴጥ. ፫፥፲፰–፲፱)።

ወደ ምድር በውሃ፣ ደምና፣ መንፈስ ተወለድክ፣ ሙሴ ፮፥፶፱። መንፈስ ከሆኑት መካከል ቆሞ ነበር፣ አብር. ፫፥፳፫።

ክፉ መንፈሶች፣ ኢየሱስ ዲያብሎሶች አወጣ፣ ማር. ፩፥፳፮፣ ፴፬፣ ፴፱። አንተ ርኵስ መንፈስ፥ ከዚህ ሰው ውጣ፣ ማር. ፭፥፪–፲፫።

እርኩስ መንፈስ ሰዎችን መፀለይ እንደሌለባቸው ያስተምራቸዋል፣ ፪ ኔፊ ፴፪፥፰። ፲በኢየሱስ ስም ዲያብሎስን እንዲሁም እርኩስ መንፈስን አስወጥቷል፣ ፫ ኔፊ ፯፥፲፱።

ብዙ የሀሰት መንፈሶች አለምን በማታለል ሄደዋል፣ ት. እና ቃ. ፶፥፪፣ ፴፩–፴፪። ጆሴፍ ስሚዝመንፈስ ከእግዚአብሔር ይሁን ወይም ከዲያብሎስ ለይቶ ለማወቅ የሚቻልበት ሶስት ዋና መንገዶችን ገልጿል፣ ት. እና ቃ. ፻፳፱።

መንፈስ ቅዱስ። *ደግሞም* መነሳሻ፣ መነሳሳት፤ ራዕይ፤ ቅዱስ የተስፋ መንፈስ፤ አፅናኝ፤ እግዚአብሔር፣ አምላክ፤ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ፤ የርግብ መልእክት፤ ይቅርታ የሌለው ኃጢያት፤ ጥምቀት፣ መጥመቅ *ተመልከቱ*

የአምላክ ሶስተኛው አባል (፩ ዮሐ. ፭፥፯፤ ት. እና ቃ. ፳፥፳፰)። እርሱም የስጋ እና አጥንት ሰውነት የሌለው የመንፈስ ሰው ነው (ት. እና ቃ. ፻፴፥፳፪)። መንፈስ ቅዱስ በብዙ ጊዜ እንደ መንፈስ ወይም እንደ እግዚአብሔር መንፈስ ይጠቆማል።

መንፈስ ቅዱስ በደህንነት አላማ ውስጥ የተለያዩ አስፈላጊ ሀላፊነቶች አለው። (፩) ስለአብ እና ወልድ ምስክር ይሰጣል (፩ ቆሮ. ፲፪፥፫፤ ፫ ኔፊ ፳፰፥፲፩፤ ኤተር ፲፪፥፵፩)። (፪) ስለሁሉም ነገሮች እውነትን ይገልጻል (ዮሐ. ፲፬፥፳፮፤ ፲፮፥፲፫፤ ሞሮኒ ፲፥፭፤ ት. እና ቃ. ፴፱፥፮)። (፫) ንስሀ የገቡትን እና የተጠመቁትን ይቀድሳል (ዮሐ. ፫፥፭፤ ፫ ኔፊ ፳፯፥፳፤ ሙሴ ፮፥፷፬–፷፰)። (፬) እርሱም ቅዱስ የተስፋ መንፈስ ነው (ት. እና ቃ. ፸፮፥፶–፶፫፤ ፻፴፪፥፯፣ ፲፰–፲፱፣ ፳፮)።

የመንፈስ ቅዱስ ሀይል ሰው ከመጠመቁ በፊት ለመምጣትና ወንጌሉ እውነት እንደሆነ ለመመስከር ይችላል። ነገር ግን ሰው ብቁ በሚሆንበት ጊዜ፣ የመንፈስ ቅዱስ የማያቋርጥ ጓደኝነት ሀይል ወደ እውነተኛዋ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ፈቃድ ከተሰጠበት ጥምቀት በኋላ በመልከ ጼዴቅ የክህነት ባለስልጣን እጅ በመጫን በኩል ለመቀበል የሚቻል ስጦታ ነው።

መንፈስ ቅዱስን ከመስደብ በስተቀር ሁሉም ኃጢያቶች ለመሰረይ ይችላሉ ብሎ ኢየሱስ አስተምሯል (ማቴ. ፲፪፥፴፩–፴፪፤ ማር. ፫፥፳፰–፳፱፤ ሉቃ. ፲፪፥፲፤ ዕብ. ፮፥፬–፰፤ ት. እና ቃ. ፸፮፥፴፬–፴፭)

መንፈስ በእግዚአብሔር ትእዛዛት ሰዎችን ያስሄዳቸዋል፣ ሕዝ. ፴፮፥፳፯።

መከራ ፳፯

ሐዋሪያት በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እንዲያጠምቁ ታዝዘዋል፣ **ማቴ.** ፳፰፡፲፱። መንፈስ ቅዱስ ሁሉን ያስተምራችኋል፣ **ዮሐ.** ፲፬፡፳፮። ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ፣ ፪ **ጴጥ.** ፩፡፳፩።

ኔፊ በመንፈስ ተመራ፣ ፩ **ኔፊ** ፬፡፮። የእግዚአብሔር ሚስጥር በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይገለጥላቸዋል፣ ፩ **ኔፊ** ፲፡፲፯–፲፱። መንፈስ ቅዱስ ማድረግ ያለባችሁን ነገሮች ሁሉ ያሳያችኋል፣ ፪ **ኔፊ** ፴፪፡፭። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሁሉንም ነገር እውነታ ታውቁታላችሁ፣ **ሞሮኒ** ፣፡፭።

መንፈስ ቅዱስ በአዕምሮህ እና በልብህ ይነግር ሃል፣ **ት. እና ቃ.** ፳፡፪። መንፈስ ወደ መልካም ይመራል፣ **ት. እና ቃ.** ፲፭፡፲፪። መንፈስ ቅዱስ ሁሉንም ነገሮች ያውቃል፣ **ት. እና ቃ.** ፴፭፡፲፱። መንፈስ ቅዱስ የመንግስተ ሰማይን የሰላም ነገሮችን ያስተምራል፣ **ት. እና ቃ.** ፴፯፡፪ (**ት. እና ቃ.** ፴፱፡፯)። መንፈስን ካልተቀበላችሁ፣ አታስተምሩም፣ **ት. እና ቃ.** ፶፪፡፲፡ መንፈስ ቅዱስ ስለአብ እና ስለወልድ ይመሰክራል፣ **ት. እና ቃ.** ፶፪፡፲፯ (፩ ቆሮ. ፲፪፡፫፣ ፣ ኔፊ ፲፭፡፴፪፣ ፴፭–፴፯)። ለአንዳንዶቹ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እንዲያውቁ በመንፈስ ቅዱስ ተሰጥቷቸዋል፣ **ት. እና ቃ.** ፶፯፡፲፣ በመንፈስ ቅዱስ ሲነሳሱ የሚናገሩት ማንኛውም ነገር ቅዱሣት መጻህፍት ይሆናል፣ **ት. እና ቃ.** ፳፯፡፭። ለምትሉት ማንኛቸውም ነገሮች ሁሉ ምስክር ለመስጠት መንፈስ ቅዱስ ይላካል፣ **ት. እና ቃ.** ፲፡፳፡ መንፈስ ቅዱስም የሁልጊዜ ጓደኛህ ይሆናል፣ **ት. እና ቃ.** ፲፳፭፡፶፭–፶፯።

መከራ። ጭንቀት *ተመልከቱ*

መከር

አንዳንድ ጊዜ ቅዱስ መጻህፍቶች *መከር* ሰዎችን በምድር ላይ የእግዚአብሔር መንግስት ወደሆነችው ወደ ቤተክርስቲያኗ እንደ ማምጣት፣ ወይም እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት አይነት ፍርድ ጊዜ እንደ ማምጣት ምሳሌአዊነት ይጠቀሙበታል።

መከሩ አልፎአል፡ በጋው ሄዶአል፡ እኛም አልዳንም፣ **ኤር.** ፰፡፳ (**ት. እና ቃ.** ፶፯፡፲፯)።

መከሩስ ብዙ ነው፡ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፣ **ማቴ.** ፱፡፴፯። መከሩም የዓለም መጨረሻ ነው፣ **ማቴ.** ፣፣፡፴፱። ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳል፣ **ገላ.** ፮፡፯–፱ (**ት. እና ቃ.** ፮፡፴፣)።

የእርሻው ስፍራ ነጭ ሆኖ ለመከር ዝግጁ ነው፣ **ት. እና ቃ.** ፬፡፬። መከሩ ያልፋል፣ እና መንፈሳችሁም አይድኑም፣ **ት. እና ቃ.** ፶፭፡፪። የመከር ጊዜ መጥቷል፣ እና ቃሌም መፈጸም አለበት፣ **ት. እና ቃ.** ፻፩፡፳፬።

መኩራት። ኩራት *ተመልከቱ*

መክሊት

የጥንት የክብደት መለኪያ ወይም ታላቅ ዋጋ ያለው ገንዘብ። ይህም እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል አይነት ታላቅ ዋጋ ስላለው ነገር ምሳሌ ሊያገለግልም ይችላል (ማቴ. ፳፭፡፲፡–፳፱፣ ኤተር ፲፪፡፴፭፣ ት. እና ቃ. ፴፡፪፣ ፣፣፣)።

መኮነን፣ ኩነኔ። *ደግሞም ዳኛ፣ ፍርድ፣ ፍርድ፣ የመጨረሻው ተመልከቱ*

መፍረድ ወይም በእግዚአብሔር እንደ ወንጀለኛ መፈረድ።

ተንኰለኛውን ሰው ግን ይቀሥፈዋል፣ **ምሳ.** ፲፪፡፪።

በተፈረደብን ጊዜ ከዓለም ጋር እንዳንኮነን በጌታ እንገሠጻለን፣ ፩ **ቆሮ.** ፲፩፡፴፪።

ቃላቶቻችን፣ ስራዎቻችን፣ እና ሀሳቦቻችን ያስኮንኑናል፣ **አልማ** ፲፪፡፲፡ ነገሮችን በማወቅና ባለማከናወን፣ ሰዎች በኩነኔ ስር ናቸው፣ **ሔለ.** ፲፡፡፲፱። እንስራ፣ መስራት ካቆምን እንኮነናለን፣ **ሞሮኒ** ፱፡፮።

ለወንድሙ ይቅርታ የማይሰጥ በጌታ ፊት ይኮነናል፣ **ት. እና ቃ.** ፳፡፱፡ በታላቅ ብርሀን ላይ ኃጢያት የሚሰራው የባሰውን ፍርድ ይቀበላል፣ **ት. እና ቃ.** ፹፪፡፫፡ ንስሀ እስከሚገቡና መፅሐፈ ሞርሞንን እስከሚያስታውሱ ድረስ ቤተክርስቲያኗን ሁሉ በፍርድ ላይ ናት፣ **ት. እና ቃ.** ፹፡፱፡–፹፯።

መወለድ። *ደግሞም አንድያ ልጅ፣ የእግዚአብሔር ወንድ እና ሴት ልጆች፣ የክርስቶስ ልጆች፣ ዳግመኛ መወለድን፣ ከእግዚአብሔር መወለድ ተመልከቱ*

መወለድ ወደ ህይወት ማምጣት በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ፣ እነዚህ ቃላቶች ብዙም ጊዜ የሚጠቀሙባቸው ከእግዚአብሔር የመወለድን ለማለት ነው። ምንም እንኳን ኢየሱስ ክርስቶስ በስጋ የአብ አንድያ ልጅ ቢሆንም፣ ሁሉም ሰዎች እርሱን በመቀበል፣ ትእዛዛቱን በማክበር፣ እና በመንፈስ ቅዱስ ሀይል በኩል አዲስ ሰዎች በመሆን ከክርስቶስ የተወለዱ ለመሆን ይችላሉ።

እኔ ዛሬ ወለድሁህ፣ መዝሙረ ዳዊት፣ **መዝ.** ፪፡፯ (የሐዋ. ፣፣፡፣፣፣ ዕብ. ፩፡፭–፮፣ ፭፡፭)።

አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር ነው፣ **ዮሐ.** ፩፡፲፡ (፪ ኔፊ ፳፭፡፲፪፣ አልማ ፲፪፡፴፣–፴፪፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፳፡፳፣)። እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአል፣ **ዮሐ.** ፣፡፲፯ (ት. እና ቃ. ፳፡፳፩)።

ክርስቶስ ህዝቦቹን በመንፈስ ወልዷቸዋል፣ **ሞዛያ** ፭፡፯።

በጌታ በኩል የተወለዱት የበኩር ቤተክርስቲያን ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፣ ፲ ፡ ፲ ፪።

መዘመር። *ደግሞም መዝሙር፤ ሙዚቃ ተመልከቱ*

እግዚአብሔርን በመዝሙር እና በሙዚቃ ግጥም ማምለክ እና ማመስገን።

ለጌታ ዘምሩ፣ ፤ ዜና ፣ ፡ ፲ ፭–፲ ፮ (መዝ. ፣ ፡ ፲ ፭)። ለእግዚአብሔር ዘምሩ፡ አመስግኑ፣ መዝ. ፡ ፡ ፡ ። ለእግዚአብሔር እልል በሉ፣ መዝ. ፡ ፡ ። መዝሙርም ከዘመሩ በኋላ ወደ ደብረ ዘይት ወጡ፣ ማቴ. ፣ ፡ ፡ ።

መንፈስ ቅዱስ እንዲዘምሩ ይመራቸዋል፣ ሞሮኒ ፣ ፡ ፡ ።

የጻድቅን መዝሙር ለእኔ ጸሎት ነው፣ ት. እና ቃ. ፣ ፡ ፡ ፡ ፡ ። ደስተኛ ከሆናችሁ፣ ጌታን በዘፈን አም ልኩ፣ ት. እና ቃ. ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ።

መዝሙረ ዳዊት። *ደግሞም ሙዚቃ፤ ዳዊት ተመልከቱ*

የተነሳሳ ግጥም ወይም መዝሙር

መዝሙረ ዳዊት፣ ብዙዎቹ ስለክርስቶስ የሆኑ፣ የመዝሙር ጥርቅሞችን የያዘ የብሉይ ኪዳን መፅ ሐፍ። መዝሙረ ዳዊት በአዲስ ኪዳን ውስጥ በብዙ ጊዜ ተጠቅሷል።

ዳዊት ብዙዎቹን መዝሙሮች ፅፏል። መዝሙ ሮቹ እግዚአብሔርን ለማሞገስ የተጻፉ ነበሩ። ብዙ ዎቹ በሙዚቃ የተዘጋጁ ነበሩ።

መዝሙር። *ደግሞም መዘመር፤ ሙዚቃ ተመልከቱ*

እግዚአብሔር የሚሞገስበት መዝሙር።

ጌታ ወደ ጌቴሴማኒ ከመሄዱ በፊት አስራ ሁለቱ ሐዋሪያት መዝሙር ዘመሩ፣ ማቴ. ፣ ፡ ፡ ።

ጌታ ኤማ ስሚዝ ቅዱስ መዝሙሮችን ለመምረጥ አዘዛት፣ ት. እና ቃ. ፣ ፡ ፡ ። የጻድቅን መዝሙር ለእኔ ጸሎት ነው፣ በረከት በራሳቸው ላይ በማድ ረግ ይመለስላቸዋል፣ ት. እና ቃ. ፣ ፡ ፡ ። ጌታን በመዝሙርና በሙዚቃ አምልኩ፣ ት. እና ቃ. ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ።

መድኃኒት። *ደግሞም አዳኝ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልከቱ*

ሁሉንም ከሞት እስርና ንስሀ የሚገቡትን ከኃጢ ያት ቅጣቶች ስለሚያድን ኢየሱስ ክርስቶስ መድኃ ኒት (ቤዛ) ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ዘር ታላቅ ቤዛ ነው፣ ምክንያቱም በኃጢያት ክፍያው በኩል እርሱ የሰው ዘር ኃጢያት ዋጋን ከፈለ እናም የሁሉ ንም ሰዎች ትንሳኤ ሊሆን እንዲቻል አደረገ።

እግዚአብሔር ዓለቴ አምባዬ መድኃኒቴ ነው፣ ፤ ሳሙ. ፣ ፡ ፤ (መዝ. ፣ ፡ ፡ ፣ ፡ ፡ ፡ ፡)። የሚ ቤዣኝ ሕያው እንደ ሆነ ያውቃል፣ ኢዮብ ፣ ፡ ፡ ። አንተ ረዳቴና መድኃኒቴ ነህ፣ መዝ. ፡ ፣ ፣ (መዝ. ፡ ፡ ፡)። እረዳሃለሁ፡ ይላል እግ ዚአብሔር፣ የሚቤዥህም የእስራኤል ቅዱስ ነው፣ ኢሳ. ፡ ፡ ፣ ፡ ፡ (ኢሳ. ፣ ፡ ፡ ፣ ፡ ፡ ፣ ፡ ፡ ፣ ፡ ፡ ፣ ፡ ፡)። እኔ እግዚአብሔር መድኃኒትሽና ታዳጊሽ ነኝ፣ ኢሳ. ፡ ፡ ፣ ፡ ፡ (ኢሳ. ፡ ፡ ፣ ፡ ፡)።

እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ፣ ማቴ. ፣ ፡ ፡ ። የሰው ልጅ ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ መጣ፣ ማቴ. ፡ ፡ ፡ ፡ (፣ ጢሞ. ፣ ፡ ፡–፣)። የእስራኤል ጌታ አምላክ ጐብኝቶ ለሕዝቡ ቤዛ አድርጎአል፣ ሉቃ. ፣ ፡ ፡ ፡ ። ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ታረቅን፣ ሮሜ ፣ ፡ ፣ ። መድኃኒት ከጽዮን ይወጣል፣ ሮሜ ፣ ፡ ፡ ። ኢየሱስ ክርስቶስ ከዓመፅ ሁሉ እንዲ ቤዣን፣ ስለ እኛ ነፍሱን ሰጥቶአል፣ ቲቶ ፣ ፡ ፣ ፡–፣ ፡ ። ኢየሱስ ክርስቶስ ከኃጢአታችንም በደሙ አጠበን፣ ራዕ. ፣ ፡ ፣ ።

ቤዛነት የሚመጣው በቅዱስ መሲሕ በኩል ነው፣ ፣ ፡ ፣ ፡–፣ ፣ ፡ ፣ ። ወልድ በእራሱ ላይ የሰውን ኃጢያት እና መተላለፍ ወሰደ፣ አዳናቸው፣ እናም የፍትህን ፍላጎት አሟላ፣ ሞዛያ ፣ ፡ ፣ ፡–፣ ፣ ፡ ፡–፣ ፡ ። ክርስቶስ ወደ ንስሀ መግባት የሚጠመቁትን ሁሉ ለማዳን መጣ፣ አልማ ፣ ፡ ፣ ፡–፣ ፡ ። ህዝቡን ለማዳንና ወደ ዓለም ይመጣል፣ አልማ ፣ ፡ ፣ ፡–፣ ፡ ። ቤዛነት በንስሃ አማካይነት ይመጣል፣ አልማ ፣ ፡ ፣ ፡–፣ ፡ ። ኢየሱስ አለምን ለማዳን መጣ፣ ሔለ. ፣ ፡ ፣ ፡–፣ ፡ ። ክርስቶስ የሰው ዘርን ከስጋዊ እና ከመን ፈሳዊ ሞት ለማዳን መጣ፣ ሔለ. ፣ ፡ ፣ ፡–፣ ፡ ። በክ ርስቶስ ቤዛነት ይመጣል፣ ፣ ፡ ፣ ፡ ፣ ፡ ። ከዓለም መፈጠር ጀምሮ ህዝቤን ለማዳን የተዘጋጀሁ እኔ ነኝ፣ ኤተር ፣ ፡ ፣ ፡ ።

ምርሞን የተባለው ቅፅል ስም የተሰጠው የቤተ ክርስቲያኗ አባል ያልሆኑት ለኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላትን ለመጠቆም ነበር። ስሙም የመጣው በጥንት ነቢይ ሞርሞን የተዘጋጀና መፅሐፈ ሞርሞን ከተባለው ቅዱሣት መጻህፍት ነው። ጌታ የቤተክርስቲያኗ አባላት እንዲጠሩበት የተሰጣቸው ስም “ቅዱሳን” ነው። የቤተክርስቲያኗ ትክክለኛ ስምም የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ነው።

ሞርሞን፣ የኔፋውያን ነቢይ። *ደግሞም መፅሐፈ ሞርሞን ተመልከቱ*

የኔፋውያን ህዝብ ነቢይ፣ የወታደሮች ጄነራል፣ እና የመፅሐፈ ሞርሞን መዝገብ ጠባቂ። ሞርሞን በ፫፻፲፭–፫፻፷፭ ም.ዓ. አካባቢ ይኖር ነበር (ሞር. ፩፡፪፣ ፯፣ ፯፡፭–፯፣ ፰፡፪–፫)። ከአስራ አምስት አመቱ ጀምሮ በብዙ ህይወቱ የወታደሮች መሪ ነበር (ሞር. ፪፡፩–፪፣ ፫፡፰–፲፪፣ ፭፡፩፣ ፰፡፪–፫)። አማሮን ሞሮኒን በመዝገቦቹ ሀላፊነት ለመው ሰድና መዝገቦችን ለመጠበቅ እንዲዘጋጅ መመሪያ ሰጠው (ሞር. ፩፡፪–፭፣ ፪፡፣ ፲፯–፲፰)። የህይወቱን ታሪክ ከመዘገበ በኋላ፣ ሞርሞን የኔፊን ታላቅ ሰሌዳ በሞርሞን ሰሌዳዎች ላይ በማሳጠር ጻፈ። በኋላም ይህን ቅዱስ መዝገብ ለልጁ ለሞሮኒ አሳልፎ ሰጠ። እነዚህ ሰሌዳዎች ጆሴፍ ስሚዝ መፅሐፈ ሞርሞንን የተረጎመባቸው ሰሌዳዎች ክፍል ነበሩ።

የሞርሞን ቃላት፣ በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ ትንሹ መፅሐፍ። በመፅሐፈ ኦምኒ ውስጥ አማሌቅ የመጨረሻ ቃላት እና በመፅሐፈ ሞሳያ የመጀመሪያ ቃላት መካከል፣ የመዝገቦቹ በሙሉ አዘጋጁ ሞርሞን ይህን ትንሽ ተጨማሪ ጻፈ። (“ስለመፅሐፈ ሞርሞን አጭር መግለጫ” በመፅሐፈ ሞርሞን መጀመሪያ ውስጥ ተመልከቱ።)

መፅሐፈ ሞርሞን፣ መፅሐፈ ሞርሞን ተብሎ በሚታወቀው ቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ የሚገኝ የተለየ መጽሐፍ። ምዕራፍ ፩–፪ የኔፋውያን ነቢይ አማሮን ሞርሞን ሰሌዳዎችን መቼና የት እንደሚያገኛቸው ስላስተማረው ይናገራሉ። ደግሞም፣ ታላቁ ጦርነት ተጀመረ፣ እናም ሶስቱ ኔፋውያን በህዝብ ክፋት ምክንያት ተወሰዱ። ምዕራፍ ፫–፪ ሞርሞን ለህዝቦቹ ንስህ ስለመግባት መስበኩ ይናገራሉ። ነገር ግን ስሜት የሚሰማቸው አልነበሩም እናም በእስራኤል ውስጥ ከነበረው ክፋት ሁሉ በላይ ታላቅ ክፋት ተባዛ። ምዕራፍ ፭–፯ በኔፋውያን እና በላማናውያን መካከል የመጨረሻ ጦርነት ይመዘግባሉ። ሞርሞን ከብዙዎቹ የኔፋውያን ህዝቦች ጋር ተገደለ። በምዕራፍ ፯ ውስጥ፣ ከመሞቱ በፊት፣ ሞርሞን እዚያ ያሉትን እና የወደፊት ህዝቦቹን ንስሀ እንዲገቡ ጠራ። ምዕራፍ ፰–፱ በመጨረሻም የሞርሞን ልጅ ሞሮኒ ብቻ በህይወት እንደቀረ ይመዘግባል። የኔፋውያን ህዝብ መጨረሻን የሚጨምር የመጨረሻውን የሞትና የጭፍጨፋ ትእይንትን መዘገበ፣ እናም ለወደፊት ትውልዶችና ይህም መዝገብ ለሚያነቡት መልእክት ጻፈ።

ሞሮኒ፣ ሻምበል። *ደግሞም የነፃነት አርማ ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ በ፪ ም.ዓ. አካባቢ የኖረ ጻድቅ የኔፋውያን የወታደሮች አዛዥ።

ሞሮኒ በኔፋውያን ወታደሮች ላይ ሙሉ በሙሉ አዛዥ ነበር፣ **አልማ** ፵፫፡፲፯–፲፯። የተነሳሱ የኔፋውያን ወታደሮች ለነጻነታቸው ተዋጉ፣ **አልማ** ፵፫፡፴፤–፴። በኮቱ ቁራጭ ላይ የነፃነት አርማ ሰራ፣ **አልማ** ፵፮፡፲፪–፲፫። የእግዚአብሔር ሰው ነበር፣ **አልማ** ፵፭፡፲፩–፲፤። የሀገራቸውን ነፃነት በተመለከተ በመንግስቱ ግዴለሽነት ተቆጥቶ ነበር፣ **አልማ** ፶፬፡፲፣ ፶፫።

ሞሮኒ፣ የሞርሞን ልጅ። *ደግሞም መፅሐፈ ሞርሞን፣ ሞርሞን፣ የኔፋውያን ነቢይ ተመልከቱ*

በመጽሐፈ ሞርሞን ውስጥ የመጨረሻው የኔፋውያን ነቢይ (በ፬፻፷፭ ዓ.ም. አካባቢ)። ከሞርሞን ሞት በፊት፣ የሞርሞን ሰሌዳዎች ተብለው የሚጠሩትን የታሪክ መዝገቦች ለልጁ ሞሮኒ ሰጠ (ቃላት ፩፡፩)። ሞሮኒ የሞርሞን ሰሌዳዎችን ማዘጋጀትን ጨረሰ። በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ ምዕራፍ ፰ እና ፱ን ጨመረ (ሞር. ፰፡፩)። መፅሐፈ ኤተርን አሳጥሮ ጻፋቸውና ጨመራቸው (ኤተር ፩፡፩–፪) እናም መፅሐፈ ሞርሞን የሚባለውን የእርሱን መፅሐፍ ጨመረ (ሞሮኒ ፩)። ሞሮኒ ሰሌዳዎችን አተመ እና በከሞራ ኮረብታ ውስጥ ደበቃቸው (ሞር. ፰፡፲፭፣ ሞሮኒ ፲፡፪)። በ፲፰፻፷፫ (እ.አ.አ.) ሞሮኒ ከሞት እንደተነሳ ሰው መፅሐፈ ሞርሞንን ለጆሴፍ ስሚዝ እንዲገልፅ ትልኮ ነበር። (ት.እና ቃ. ፳፯፡፩፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፴–፴፪፣ ፴፯)። ወጣቱን ነቢይ ከ፲፰፻፷፫ እስከ ፲፰፻፷፯ (እ.አ.አ.) አስተማረው

መፅሐፈ ሞዛያ፣ በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ የሚገኝ መፅሐፍ። ምዕራፍ ፩–፯ ንጉስ ቢንያም ለሕዝቡ የሰጠውን ሀይለኛ ስብከት የያዙ ናቸው። የጌታ መንፈስ ልባቸውን ነካቸው እና ህዝቡም ተቀየሩ፣ እንዲሁም ክፉ ለማድረግ ምንም ፍላጎት አይሰማቸውም። ምዕራፍ ፯–፰ በላማናውያን ምድር ለመኖር ስለሄዱ የኔፋውያን ቡድን ይናገራሉ። የሚፈልጓቸው ቡድን መሪ አሞን አገኛቸው እናም በላማናውያን ጭቆና ስር ስለነበራቸው ፈተናዎች ታሪክ ተማረ። ምዕራፍ ፱–፳፪ ያን ጭቆና እና እንዴት መሪአዎቻቸው ዜኒፍ፣ ኖኅ፣ እና ሊምሂ በላማናውያን ስር እንደ ኖሩ ይገልጻሉ። አቢናዲ ተብሎ የሚጠራው ነቢይ ሰማዕትም ተመዝግቧል። አልማ አቢናዲ ለፍርድ በቀረበበት ጊዜ ተቀየረ። ምዕራፍ ፳፭–፳፰ የአልማ ልጅ እና የንጉስ ሞዛያ አራት ልጆች እንዴት እንደተቀየሩ ታሪክን ይነግራሉ። በምዕራፍ ፳፱ ውስጥ ንጉስ ሞዛያ የመሳፍንት መንግስት ንጉሶችን እንዲ ተኩ ሀሳብ አቀረበ። የአልማ ልጅ አልማ ዋና ዳኛ እንዲሆን ተመረጠ።

ሞዛያ፣ የቢንያም አባት። *ደግሞም* ቢንያም፣ የሞዛያ አባት፤ ዛራሔምላ *ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ በዛራሔምላ ህዝብ ላይ ንጉስ እንዲሆን የተደረገ የኔፋውያን ነቢይ።

ከኔፊ ምድር እንዲወጣ ተጠነቀቀ፣ **ኦምኒ** ፩፡፲፪። የዛራሔምላ ህዝብን አገኘ፣ **ኦምኒ** ፩፡፲፰–፲፭። የዛራሔምላ ህዝብ የእርሱን ቋንቋ እንዲማሩ አደረገ፣ **ኦምኒ** ፩፡፲፭። በአንድነት የተዋሃዱ ህዝብ ንጉስ እንዲሆን ተመደበ፣ **ኦምኒ** ፩፡፲፱። ከሞተ በኋላ፣ ልጁ ቢንያም በምትኩ ነገሰ፣ **ኦምኒ** ፩፡፳፫።

ሚኪ አባት። *ደግሞም* ቤተሰብ፤ ወላጆች፤ የአባቶች አለቃ፣ ፓትሪያርክ፤ የፓትሪያርክ በረከቶች *ተመልከት*

ልጅን ለወለደ ወይም በጉዲፈቻ ላሳደገ ሰው የሚሰጥ ቅዱስ ርዕስ።

አባትህንና እናትህን አክብር፣ **ዘፀአ.** ፳፡፲፪ (ዘዳግ. ፭፡፲፮፣ ማቴ. ፲፱፡፲፱፣ ሞዛያ ፲፫፡፳)። አባት የሚወደውን ልጁን እንደሚገሥጽ፣ **ምሳ.** ፫፡፲፪።

አባቶች ሆይ፡ አታስቆጡአቸው፣ **ኤፌ.** ፮፡፩–፬።

አባቴ ከሚያውቃቸው በመጠኑ ተማርኩ፣ **ፊ ኔፊ** ፩፡፩። አባቴ ፃድቅ ሰው ነበር—አስተማሮኛልና፣ **ኢኖስ** ፩፡፩። አልማ ለልጁ ጸለየ፣ **ሞዛያ** ፳፯፡፲፬። አልማ ለልጆቹ ትእዛዛትን ሰጠ፣ **አልማ** ፴፯–፴፱። ሔለመን ልጆቹን የቅድመ አያቶቹን ስም ሰጣቸው፣ **ሔለ.** ፭፡፮–፲፪። ሞርሞን ልጁን በጸሎቱ ሁልጊዜ ያስታውሳል፣ **ሞሮኒ** ፰፡፪–፫።

(ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፶፩) እና በመጨረሻም በ፲፰፻፳፯ (እ.አ.አ.) ሰሌዳዎችን ለእርሱ ሰጠው (ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፶፩)። መተርጎምን ከጨረሰ በኋላ ጆሴፍ ስሚዝ ሰሌዳዎችን ለሞሮኒ መለሰ።

መፅሐፈ ሞሮኒ፣ በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ የመጨረሻው መፅሐፍ። የተጻፈው በኔፋውያን የመጨረሻ ነቢይ ሞሮኒ ነበር። ምዕራፍ ፩–፫ ስለኔፋውያን የመጨረሻ መደምሰስ ይናገራሉ፣ መንፈስ ቅዱስን እና ክህነትን ስለመስጠት መመሪያ ይሰጣሉ። ምዕራፍ ፬–፭ የቅዱስ ቁርባንን ማስተዳደር ዘዴን ይገልጻሉ። ምዕራፍ ፮ የቤተክርስቲያናን ስራ በማጠቃላል ይገልጻል። ምዕራፍ ፯–፰ ከሞርሞን የእምነት፣ ተስፋና፣ ልግስና ትምህርት እና ጥሩን ከመጥፎ ስለመፍረድ መንገድ በተጨማሪ የወንጌልን ቀዳሚ መሰረታዊ መርሆች (ሞሮኒ ፯)፣ እናም ትንሽ ልጆች በክርስቶስ ሀያው የሆኑና ጥምቀት እንደማያስፈልጋቸው ሞሮኒ የገለጸበት (ሞሮኒ ፰) ስብከቶች ናቸው። ምዕራፍ ፱ የኔፋውያን ህዝቦች በስነምግባር የጎደለ እንደነበረ ይገልጻል። ምዕራፍ ፲ የሞሮኒ የመጨረሻ መልእክት ነው እናም በተጨማሪ መፅሐፈ ሞርሞን እውነት እንደሆነ የሚታወቅበትን መንገድ ይገልጻል (ሞሮኒ ፲፡፫–፮)።

ሞሮኒሀ፣ የሻንበል ሞሮኒ ልጅ

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ ጻድቅ የኔፋውያን አዛዥ (በ፰ ዓ.ዓ. አካባቢ)።

ሞሮኒ ሞሮኒሀ ተብሎ ለሚጠራው ልጁ የሠራዊቱን መሪነት አሳልፎ ሠጠ፣ **አልማ** ፰፡፭፡፴፫። የዛራሔምላን ከተማ በድጋሚ ወሰደ፣ **ሔለ.** ፩፡፴፫። ኔፋውያን ንስሀ እንዲገቡ አደረገ እናም በምድር ግማሽ ላይ ቁጥጥርን በዳግም አገኘ፣ **ሔለ.** ፬፡፲፬–፳።

ሞአብ። *ደግሞም* ሎጥ *ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ጊዜ በሙት ባህር በስተምስራቅ በኩል የሚገኝ ምድር። ሞዓባውያን የሎት ትውልዶች ነበሩ እናም ከእስራኤላውያን ጋር ዘመድ ነበሩ። ከዕብራውያን ቋንቋ ጋር የሚመሳሰል ቋንቋ ነበራቸው። በሞአባውያንና በእስራኤላውያን መካከል የማይቆም ጦርነት ነበረ (መሳ. ፫፡፲፪–፴፣ ፲፩፡፲፣ ፲፯፡፲፣ ፪ ሳሙ. ፰፡፪፣ ፪ ነገሥ. ፫፡፭–፳፯፣ ፪ ዜና ፳፡፩–፳፭፣ ኢሳ. ፲፭)።

ሞዛያ፣ የቢንያም ልጅ። *ደግሞም* ቢንያም፣ የሞዛያ አባት፤ የሞዛያ ልጆች *ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ የኔፋውያን ጻድቅ ንጉስ እና ነቢይ። ሞዛያ የአባቱን ጻድቅ ምሳሌ ተከተለ (ሞዛያ ፤፡፩–፯)። የያሬዳውያን መዝገቦችን የያዙትን ሀያ አራት የወርቅ ሰሌዳዎች ተረጎመ (ሞዛያ ፳፰፡፲፯)።

ታላላቅ ነገሮች ከአባቶቻቸው እጅ ይጠበቃል፣ ት. እና ቃ. ፯፤፱፡፳፯። ቤተሰቡን የማስተዳደር ሀላፊነት እያንዳንዱም ሰው አለበት፣ ት. እና ቃ. ፹፭፡፳፯።

ወደ አባቴ እንድሄድ አዘዘኝ፣ ጆ.ስ.—ታ. ፭፡፳፱።

ሩት። *ደግምም ቦኤዝ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ እስራኤላውያን ለሆኑት ኑኃሚ እና አቢሜሌክ አማች የነበረች የሞአብ ሴት። ከባሏ ሞት በኋላ፣ ሩት የኒኃሚን ዘመድ ቦዔዝን አገባች። ልጃቸው ኢዮቤድ የዳዊት እና የክርስቶስ ትውልድ ነበር። የሩት ታሪክ እስራኤላዊ ያልሆነችውን ወደ እስራኤል እቅፍ መቀየርን በደንብ ያሳያል። ሩት የድሮ ጣዖቷን እና የድሮ ህይወቷን የእስራኤል እግዚአብሔርን ከሚያገለግል የእምነት ቤት ጋር አንድ ለመሆን ተወች (ሩት ፩፡፲፮)።

መፅሐፈ ሩት፣ ምዕራፍ ፩ በሞአብ ውስጥ የነበራቸውን የአቢሜሌክ እና የቤተሰቡን ህይወት ይገልጻል። ከባላቸው ሞት በኋላ፣ ኑኃሚ እና ሩት ወደ ቤተልሔም ሄዱ። ምዕራፍ ፪ ሩት ከቦዔዝ ሜዳ ውስጥ እንደ ቃረመች ይገልጻል። ምዕራፍ ፫ ኑኃሚ ሩትን ወደ አውድማ እንድትሄድ እና በቦዔዝ እግር ስር እንድትወድቅ እንዳስተማረቻት ይናገራል። ምዕራፍ ፬ የሩት እና የቦዔዝ ጋብቻ ታሪክ ነው። ኢዮቤድ የሚባል ወንድ ልጅ ወለዱ፣ በእርሱም ትውልድ ዳዊት እና ክርስቶስ ተወለዱ።

ሪግደን፣ ስድኒ

በ፲፰፻፱ እና በ፲፰፻፹ (እ.አ.አ.) መጀመሪያ መካከል በዳግም በተመለሰችው ቤተክርስቲያን ውስጥ በመጀመሪያ የተቀየረ እና መሪ የነበረ ሰው። ስድኒ ሪግደን ለአንድ ጊዜ በቤተክርስቲያኗ ቀዳሚ አመራር ውስጥ የጆሴፍ ስሚዝ የመጀመሪያ አማካሪ ነበር (ት. እና ቃ. ፴፭፣ ፴፰፡፱፣ ፴፱፣ ፵፫፡፴፭–፴፮፣ ፹፭፡፲፭–፲፰፣ ፲፱–፳፫፣ ፶፡፮፣ ፶፭፡፴፬፣ ፹፬፡፲–፲፭)። በኋላም ወደቀ እናም በመስከረም ፲፰፻፴፬ (እ.አ.አ.) ተወገዘ።

ራሔል። *ደግምም ያዕቆብ፣ የይስሐቅ ልጅ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የያዕቆብ ሚስት (ዘፍጥ. ፳፱–፴፭፣ ፴፯)። ደግሞም የዮሴፍ እና የቢንያም እናት ነች።

ራሜዩምጵቶም

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ ሀይማኖትን የካዱት ኔፋውያን የሆኑት ዞራማውያን የጸለዩበት ከፍ ያለ የመቆሚያ ቦታ (አልማ ፴፭፡፳–፲፱፣ ፳፭)።

ራዕይ። *ደግምም ህልም፤ መነሳሻ፣ መነሳሳት፤ መንፈስ ቅዱስ፤ ብርሀን፣ የክርስቶስ ብርሀን፤ ትንቢት፣ መተንበይ፤ የመጀመሪያው ራዕይ፤ የእግዚአብሔር ቃል፤ ድምፅ ተመልከቱ*

እግዚአብሔር በምድር ላይ ካሉት ልጆቹ ጋር የሚነጋገርበት። በመንፈስ ቅዱስ ሀይል በኩል የአንድ ድርጊት፣ ሰው፣ ወይም ነገር የሚታይ ራዕይ። ራዕይ በክርስቶስ ብርሀን ወይም በመንፈስ ቅዱስ በኩል በማነሳሳት፣ በራዕዮች፣ በህልሞች፣ ወይም በመላእክት በመትብገት ሊመጣ ይችላል። ራዕይ ታማኝን በሰለስቲያል መንግስት ወደ ዘለአለማዊ ደህናነት ለመምራት የሚችል መመሪያን ይሰጣል።

ጌታ ስራውን ለነቢያቱ ይገልጻል እናም ለነቢያቱ የተሰጡት ራዕዮች እውነት እንደሆኑም ለሚያምኑት ያረጋግጣል (ዓሞ. ፫፡፯)። በራዕይ በኩል፣ ጌታ ለሚፈልገው እና እምነት ላለው፣ ንስሀ ለገባው፣ እንዲሁም ለኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ታዛዥ ለሆነው ለእያንዳንዱ ሰው መመሪያ ይሰጣል። ጆሴፍ ስሚዝ እንዳለው፣ "መንፈስ ቅዱስ ገላጭ ነው፣ ማንም ሰው ራዕይን ሳይቀበል መንፈስ ቅዱስን መቀበል አይችልም።"

በጌታ ቤተክርስቲያን ውስጥ፣ የቀዳሚ አመራር እና የአስራ ሁለቱ ሐዋሪያት ቡድን ለቤተክርስቲያኗ እና ለአለም ነቢያት፣ ባለራዕዮች፣ እና ገላጮች ናቸው። ጌታ ለቤተክርስቲያኗ ራዕይ ለመቀበል ስልጣን የሰጠው ለቤተክርስቲያኗ ፕሬዘደንት ብቻ ነው (ት. እና ቃ. ፳፯፡፪–፭)። እያንዳንዱ ሰው ለእራሱ ጥቅም ራዕይ ለመቀበል ይችላል።

ሕዝቅኤል ስለመጨረሻው ቀናት ያየው ራዕይ (ሕዝ. ፴፯–፴፱)፣ እስጢፋኖስ ኢየሱስን በእግዚአብሔር ቀኝ እጅ በኩል ቆሞ ያየው ራዕይ (የሐዋ. ፯፡፶፭–፶፮)፣ የመጨረሻው ቀናትን በሚመለከት ዮሐንስ ያየው ራዕይ (ራዕ. ፩–፳፩)፣ ሌሂ እና ኔፊ ስለህይወት ዛፍ ያዩት ራዕይ (፩ ኔፊ ፰፣ ፲–፲፪)፣ ዳግማዊ አልማ የጌታ መልአክን ያየበት ራዕይ (ሞዛያ ፳፯)፣ የያሬድ ወንድም የአለምን ኗሪዎችን ሁሉ ያየበት ራዕይ (ኤተር ፫፡፳፭)፣ የክብሮች ራዕይ (ት. እና ቃ. ፹፯) በክርትላንድ ቤተመቅደስ ውስጥ ጆሴፍ ስሚዝ እና ኦሊቨር ካውደሪ የተሰጣቸው ራዕይ (ት. እና ቃ. ፻፲)፣ ጆሴፍ ኤፍ ስሚዝ ስለሙታን ቤዛነት ያዩት ራዕይ (ት. እና ቃ. ፻፴፯)፣ ስለእግዚአብሔር እና ስለፍጥረቶቹ ለሙሴ የተሰጠ ራዕይ (ሙሴ ፩)፣ ስለእግዚአብሔር ሔሞክ ያየው ራዕይ (ሙሴ ፮–፯)፣ እና የጆሴፍ ስሚዝ የመጀመሪያ ራዕይ (ጆ.ስ.—ታ. ፩)።

ሰውም ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ነገር ሁሉ በሕይወት ይኖራል፣ ዘዳግ. ፰፡፫ (ማቴ. ፬፡፬፣ ት. እና ቃ. ፶፯፡፲፩)። ጌታ በትንሽ የዝምታ ድምፅ ይናገራል፣ ፩ ነገሥ. ፲፱፡፲፪። ራዕይ ባይኖር ሕዝብ መረን ይሆናል፣ ምሳ. ፳፱፡፲፰። ጕበዞቻችሁም

ራዕይ ያያሉ፣ ኢዩ. ፪፡፳፰ (የሐዋ. ፪፡፲፯)። በእ ውነት ጌታ እግዚአብሔር ምሥጢሩን ለባሪያዎቹ ለነቢያት ካልነገረ በቀር ምንም አያደርግም፣ ዓሞ. ፫፡፯።

የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ፣ ማቴ. ፲፮፡፲፫–፲፱። መንፈስ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፤ የሚመጣውንም ይነግራች ኋል፣ ዮሐ. ፲፮፡፲፫። ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው፥ እግዚአብሔርን ይለምን፣ ያዕ. ፩፡፭።

በራዕይ እውቀትን ሰጥቶኛል፣ ፤ ኔፊ ፬፡፳፫። ሁሉም ነገሮች ይገለፃሉ፣ ፤ ኔፊ ፳፯፡፲፩። ለሰው ልጆች በስርዐት ላይ ስርዐት እሰጣለሁ፣ ፤ ኔፊ ፳፯፡፴፡ ያልተገለጠ፣ ሚስጥር የሆነ ምንም የለም፣ ፤ ኔፊ ፴፡፲፯። መንፈስ ቅዱስ ነገሮችን ሁሉ ያሳያ ችኋል፣ ፤ ኔፊ ፴፤፡፭። ለእርሱ ካልተገለፀለት በቀር ማንም ሰው የእግዚአብሔርን መንገድ አያውቅም፣ ያዕቆ. ፬፡፰። አልማ ለራዕይ ለብዙ ቀናት ያመ እንዲሁም ፀለየ፣ አልማ ፭፡፴፯። ተገልፀው የማያው ቁት ነገሮች ለታማኞች ይገለጻሉ፣ አልማ ፳፯፡፳፤ ራዕይን የሚክዱ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልን አያ ውቁም እናም ቅዱሳት መጻህፍት አልተረዱም፣ ሞር. ፱፡፯–፰። እምነታችሁ እስከሚፈተን ድረስ ምስክርነትን አትቀበሉም፣ ኤተር ፲፤፡፯።

ቃሌ ይፈጸማል፣ ት. እና ቃ. ፩፡፴፰። ይህ ንን ነገር በተመለከተ በአምሮህ ሰላምን አልተናገ ርኩም፣ ት. እና ቃ. ፯፡፳፤–፳፫። በአዕምሮህ እና በልብህ እነግርሃለሁ፣ ት. እና ቃ. ፰፡፭–፮። ትክ ክለኛ ከሆነ በውስጥህ ልብህ እንዲቃጠል አደርጋ ለሁ፣ ት. እና ቃ. ፱፡፰። የራዕይ መንፈስንም አት ካድ፣ ት. እና ቃ. ፲፩፡፳፩። ከጠየቃችሁ፣ በራዕይ ላይ ራዕይን ትቀበላላችሁ፣ ት. እና ቃ. ፴፤፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ሲነሳሱ የሚናገሩት የጌታ ፈቃድም ይሆናል፣ ት. እና ቃ. ፳፰፡፱። እግዚአብሔር እው ቀቱን ይሰጣችኋል፣ ት. እና ቃ. ፲፳፩፡፳፯።

ጆሴፍ ስሚዝ አብን እና ወልድን አየ፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፲፯። እርሱም ከእግዚአብሔር ፊት የተላከ መል እክተኛ ነበር፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፴፫። በትንቢቶች፣ ራዕዮች እናምናለን፣ እ.አ. ፩፡፯። እግዚአብሔር እንደገለጸ እና ወደፊትም እንደሚገልፅ እናምና ለን፣ እ.አ. ፩፡፯፣ ፱።

ራጉኤል። ዮቶር *ተመልከቱ*

ራፋኤል። *ደግሞም መላእክት ተመልከቱ*

በሁሉም ነገሮች በዳግም መመለስ የተሳተፈ የእ ግዚአብሔር መልአክ (ት. እና ቃ. ፲፳፯፡፳፩)።

ርህራሄ። *ደግሞም ልግስና፣ መሀሪ፣ ምህረት፣ ፍቅር ተመልከቱ*

በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ፣ ርህራሄ ማለት "ከሌላ ጋር መሰቃየት" ማለት ነው። ደግሞም የሀ ዘን ተካፋይነትን፣ የሀዝን ስሜትን፣ እና ምህረትን ማሳየት ማለት ነው።

ጌታ ህዝቡ ሩህሩህ እንዲሆኑ ጠራቸው፣ ዘካ. ፯፡፰–፲።

ኢየሱስ አዘነላቸው፣ ማቴ. ፱፡፴፮ (ማቴ. ፳፡፴፬፣ ማር. ፩፡፴፩፣ ሉቃ. ፯፡፲፫)። አንድ ሳም ራዊ አዘነለት፣ ሉቃ. ፲፡፴፫። አንዳችሁ ለሌላችሁ ርኅሩኆችና ሁኑ፣ ፩ ጴጥ. ፫፡፰።

ክርስቶስ ለሰዎች ልጆች በርህራሄ ይሞላል፣ ሞዛያ ፲፭፡፱። አንጀቴ ለእናንተ በርህራሄ ተሞ ልቷል፣ ፫ ኔፊ ፲፯፡፮።

ጆሴፍ ስሚዝ ለጌታ ርህራሄ ጸለየ፣ ት. እና ቃ. ፲፳፭፡፫–፭።

ርብቃ። *ደግሞም ይስሐቅ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ የአባቶች አለቃው ይስሐቅ ባለቤት (ዘፍጥ. ፳፬–፳፯)። ርብቃ የዔሳው እና የያዕ ቆብ እናት ነበረች (ዘፍጥ. ፳፭፡፳፫–፳፯)።

ርኩስ። ንጹህ እና ርኩስ *ተመልከቱ*

ሮሜ። *ደግሞም የሮሜ ግዛት ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ በጣሊያን ውስጥ በጥብር ያዶስ ወንዝ አጠገብ የሚገኝ የሮሜ መንግስት ዋና ከተማ (የሐዋ. ፲፰፡፪፣ ፲፱፡፳፣ ፳፫፡፲፩)። ጳው ሎስ የሮሜ መንግስት እስረኛ በነበረ ጊዜ ወንጌሉን በሮሜ ውስጥ አስተማረ (የሐዋ. ፳፰፡፲፩–፴፩፣ ሮሜ ፩፡፯፣ ፲፭–፲፮)።

ሮቤል። *ደግሞም እስራኤል፣ ያዕቆብ፣ የይስሐቅ ልጅ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የያዕቆብ እና የልያ የመ ጀመሪያ ልጅ (ዘፍጥ. ፳፱፡፴፪፣ ፴፭፡፳–፳፪፣ ፳፱፣ ፴፪፡፳፪፣ ፴፯)። ሮቤል በኩር ቢሆንም፣ በኃ ጢያት ምክንያት በኩሩን አጣ (ዘፍጥ. ፴፭፡፳፪፣ ፴፱፡፫–፴)።

የሮቤል ጎሳ፣ ያዕቆብ ለሮቤል የሰጣቸው በረ ከቶች በኦሪት ዘፍጥረት ፴፱፡፫ እና ኦሪት ዘዳግም ፴፫፡፮ ውስጥ ይገኛሉ። የጎሳው ቁጥር ጥቂት በጥ ቂት እየቀነሰ መጣ፣ እናም ምንም እንኳን ጎሳው ቢኖርም፣ በፖለቲካ አስፈላጊነታቸው ታናሽ ነበር። የሮቤል በኩራት ለዮሴፍ እና ለልጆቹ ሆነ ምክንያ ቱም ዮሴፍ የያዕቆብ ሁለተኛ ሚስት የራሔል በኩር ስለነበረ ነው (፩ ዜና ፭፡፩–፪)።

ሮብዓም። *ደግሞም ሰለሞን ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የንጉስ ሰለሞን ልጅ። አባቱን ተካ እናም በኢየሩሳሌም ውስጥ ነገሰ (፩ ነገሥ. ፲፩፡፴፫፣ ፲፬፡፳፩፣ ፴፩)። በሮብዓም ዘመነ መንግስት፣ መንግስቱ በሰሜን ወደ እስራ

ኤል መንግስት እና በደቡብ ወደ ይሁዳ መንግስት ተከፋፈለ (፩ ነገሥ. ፲፩፡፴፭–፴፯፣ ፲፪፡፲፱–፳)። ሮብዓም የይሁዳ መንግስትን ገዛ።

ሰለሞን። *ደግምም* ቤርሳቤህ፣ ዳዊት *ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የዳዊት እና የቤርሳቤህ ልጅ (፪ ሳሙ. ፲፪፡፳፬)። ሰለሞን ለጊዜ የእስራ ኤል ንጉስ ነበር።

ዳዊት ሰለሞንን እንደ ንጉስ መደበ፣ ፩ ነገሥ. ፩፡፲፩–፶፣ ዳዊት ሰለሞንን በጌታ መንገዶች በቅ ንነት እንዲራመድ አዘዘው፣ ፩ ነገሥ. ፪፡፩–፱። ጌታ የማስተዋል ልብ እንደሚኖረው ቃል ኪዳን ሰጠው፣ ፩ ነገሥ. ፫፡፭–፲፭። በሁለት እናቶች መካከል ፈረደ እናም የልጁን እውነተኛ እናትን አረጋገጠ፣ ፩ ነገሥ. ፫፡፲፮–፳፰። ምሳሌዎችንና መኃልዩንም ተናገረ፣ ፩ ነገሥ. ፬፡፴፪። ቤተመቅደስን ገነባ፣ ፩ ነገሥ. ፮፣ ፯፡፲፣–፶፩። ቤተመቅደስን ቀደሰ፣ ፩ ነገሥ. ፰። በሳባ ንግስት ተጎበኘ፣ ፩ ነገሥ. ፣፡፩–፣፣፡። ሰለሞን ከእስራኤል ውጪ አገባ፣ እናም ሚስቶቹም የሀሰት መላእክቶችን ወደማምለክ ልቡን አዞሩ፣ ፩ ነገሥ. ፣፩፡፩–፰። ጌታ በሰለሞን ላይ ተቆጣ፣ ፩ ነገሥ. ፣፩፡፱–፣፣፡። ሞተ፣ ፩ ነገሥ. ፣፩፡፴፣፡። ዳዊት ስለ ሰለሞን ጋዛት ግርማ ተነበየ፣ መዝ. ፷፪።

ሰለሞን ብዙ ሚስቶች እና እቁባቶችን ተቀበለ፣ ነገር ግን አንዳንዶቹ ከጌታ የተቀበላቸው አልነበ ሩም፣ ት. እና ቃ. ፲፴፪፡፴፰ (ያዕቆ. ፪፡፳፭)።

ሰላም። *ደግምም* ሰላም የሚሰራ፣ አንድ ሺህ አመት፣ እረፍት *ተመልከቱ*

በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ፣ ሰላም ከጸብ እና ብጥበጣ ነጻ መሆን ወይም ለታማኝ ቅዱሳኑ እግዚ አብሔር በሚሰጠ መንፈስ የሚመጡ የውስጥ መረ ጋጋት እና ምቾት ማለት ነው።

ከጥላቻ እና ከብጥበጣ ነጻ መሆን፣ ጦርንም ይቄርጣል፣ መዝ. ፴፮፡፱። ሰልፍም ከእንግዲህ ወዲህ አይማሩም፣ ኢሳ. ፪፡፬።

ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ፣ ራሳችሁ አት በቀሉ፣ ሮሜ ፲፪፡፣፡–፳፩።

በምድሪቱ ሠላም ሰፈነ፣ ፬ ኔፊ ፩፡፬፣ ፣፲–፳።

ጦርነትን አስወግዱና ሰላም አውጁ፣ ት. እና ቃ. ፣፲፡፣፣ ፣፣፮። የሰላም ምልክት ያንሱ፣ ት. እና ቃ. ፣፲፩፡፴፱።

ለታዛዥ ከእግዚአብሔር የሚመጣ ሰላም፣ አዳኝ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል፣ ኢሳ. ፱፡፮። ለክፉ ዎች ሰላም የላቸውም፣ ኢሳ. ፴፣፡፳፪።

ብዙ የሰማይ ሠራዊት ከመልአኩ ጋር እግዚአ ብሔርንም እያመሰገኑ ክብር ለእግዚአብሔር በአ ርያም ይሁን ሰላምም በምድር አሉ፣ ሉቃ. ፪፡፣፣–፣፬። ሰላምን እተውላችኋለሁ፣ ዮሐ. ፣፬፡፳፯። የእ ግዚአብሔር ሰላም አሳባችሁን ይጠብቃል፣ ፊልጵ. ፬፡፯።

የንጉስ ቤንያምህዝብ የሀሊና ሰላምን ተቀበሉ፣ ሞዛያ ፪፡፣። በተራራው ላይ ሰላምን የሚያውጁት እግራቸው እንዴት ያማረ ነው፣ ሞዛያ ፣፲፡፣፬–፣፣ (ኢሳ. ፶፪፡፯)። አልማ ወደ ጌታ ጮኸ እናም ሰላ ምን አገኘ፣ አልማ ፴፣፡፣። የዓድቃኖች መንፈስ ወደ ሰላም ቦታ ይገባሉ፣ አልማ ፴፣፡፲፪።

ይህንን ነገር በተመለከተ በአምሮህ ሰላምን አል ተናገርኩም፣ ት. እና ቃ. ፣፯፡፣፣። ከእኔ ተማር፣ እናም ቃላቴን አድምጥ፣ በመንፈሴ በትህትና ተጓዝ፣ እናም በእኔ ሰላምን ታገኛለህ፣ ት. እና ቃ. ፣፲፱፡፣፣። የጻድቅ ስራ የሚሰራው ሰላም ይቀበላል፣ ት. እና ቃ. ፶፱፡፣፣። የፍጹምነትና የሰላም ማሰ ሪያ በሆነው በልግስና ማሰሪያ ራሳችሁን አልብሱ፣ ት. እና ቃ. ፲፣፡፣ ፣፣፣፩። ልጄ፣ በነፍስህ ሰላም ይኑርህ፣ ት. እና ቃ. ፣፣፣፩፡፣። ታላቅ ሰላም እንዳሉም ስላወኩኝ፣ የአባቶችን በረከቶች ለማግኘት ፈለኩኝ፣ አብር. ፩፡፪።

ሰላም የሚሰራ። *ደግምም* ሰላም *ተመልከቱ*

ሰላምን የሚያመጣ ወይም የሚያበረታታ ሰው (ማቴ. ፭፡፱፣ ፣ ኔፊ ፣፪፡፱)። የሰላም የሚሰራ ወን ጌልን የሚያውጅ ሊሆንም ይችላል (ሞዛያ ፣፲፩፡፣፩–፣፣)።

ሰሌዳዎች። *ደግምም* መፅሐፈ ሞርሞን፣ የወርቅ ሰሌዳዎች *ተመልከቱ*

መፅሐፈ ሞርሞን እንደነበረው፣ በጥንት ጊዜ አን ዳንድ ባህሎች ታሪካቸውንና መዝገባቸውን በብ ረት ሰሌዳዎች ላይ ይጽፉ ነበር። ለተጨማሪ መዝገ ቦች፣ በመፅሐፈ ሞርሞን ማስተዋወቂያ ገጾች ውስጥ "ስለመፅሐፈ ሞርሞን አጭር መግለጫ" የሚለውን ተመልከቱ።

ሰማርያ። *ደግምም* ሳምራዊ *ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የሰሜን እስራኤል መን ግስት ዋና ከተማ (፩ ነገሥ. ፣፮፡፳፣–፳፬)። በኮረ ብታ ላይ በነበራት ጠንካራ ወታደራዊ ቦታ፣ አሶር እስከ ሶስት አመት በጦር ከበባ ድረስ እርሷን ለመ ያዝ አልቻሉም ነበር (፪ ነገሥ. ፣፯፡፭–፮)። ሄሮድስ እንደገና ገነባት እና ሰባስቴ ብሎ ጠራት። በአዲስ ኪዳን ጊዜ ውስጥ፣ ሰማርያ በዮርዳኖስ በስተምዕ ራብ ለሚገኘው የፍልስጥኤም አውራጃ በሙሉ የተ ሰጠ ስም ነው።

ሰማዕት፣ ሰማዕትነት

ክርስቶስን፣ ወንጌልን፣ ወይም ጻድቅ እምነቱን ወይም መሰረታዊ መርሆቹን ከመካድ ህይወቱን አሳ ልፎ የሚሰጥ ሰው።

ከጻድቁ ከአቤል ደም ጀምሮ እስከ ዘካርያስ ደም

ድረስ በምድር ላይ የፈሰሰው የጻድቅ ደም ሁሉ በክፉዎች ላይ ይመሰክራሉ፣ ማቴ. ፳፫፡፴፭ (ሉቃ. ፲፩፡፶)። ስለ ክርስቶስና ስለ ወንጌል ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ያድናታል፣ ማር. ፰፡፴፭ (ት. እና ቃ. ፶፰፡፲፫)። እስጢፋኖስን ወገሩት፣ የሐዋ. ፯፡፶፱ (የሐዋ. ፳፪፡፳)። ኑዛዜ ያለ እንደሆነ የተናዛዥን ሞት ማርዳት የግድ ነው፣ ዕብ. ፱፡፲፮–፲፯።

አቢናዲ በእሳት ሞቶ ወደቀ፣ ሞዛያ ፲፯፡፳። የተቀየሩት አሞኒሀውያን ወደ እሳት ተጣሉ፣ አልማ ፲፭፡፳–፲፩። ብዙዎች ስለእነዚህ ነገሮች በመመስከራቸው ተገድለዋል፣ ፫ ኔፊ ፲፡፲፭።

ለምክንያቱ ህይወቱን የሚሰጥም ስለአለማዊ ህይወትን ያገኘዋል፣ ት. እና ቃ. ፶፰፡፲፫–፲፭። ጆሴፍ ስሚዝ እና ሐይረም ስሚዝ በዳግም ለተመለሰው ወንጌል ሰማዕት ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፲፱፡፲፭። ጆሴፍ ስሚዝ ምስክሩን በደሙ አተመ፣ ት. እና ቃ. ፲፱፡፲፮፡ ፴፱።

ሰማይ። *ደግሞም የሰለስቲያል ክብር፤ የእግዚአብሔር መንግስት ወይም መንግስተ ሰማያት፤ ገነት ተመልከቱ*

በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ ሰማይ ሁለት ትርጉሞች አሉት። (፩) እግዚአብሔር የሚኖርበት ቦታ እና የቅዱሳን የወደፊት ቤት (ዘፍጥ. ፳፰፡፲፪፤ መዝ. ፲፩፡፬፤ ማቴ. ፮፡፱)። (፪) ምድርን የሚከብ ሰፊና ገላጣ ቦታ (ዘፍጥ. ፩፡፩፤ ፲፯፤ ዘፀአ. ፳፬፡፲)። ሰማይ በዚህ ምድር ላይ በፅድቅ በመሆን የኖሩ እናም የሞቱ ታማኝ መንፈሶች ለጊዜአዊ የሚገኙበት ቦታ የሆነው ገነት እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ኢየሱስ በመስቀል ላይ ከሞተ በኋላ ገነትን ጎበኘ፣ ነገር ግን በሶስተኛው ቀን ወደ አብ ገና እንዳልሄደ ለማርያም ነግሯት ነበር (ሉቃ. ፳፫፡፴፱–፴፪፤ ዮሐ. ፳፡፲፯፤ ት. እና ቃ. ፲፴፯፡፲፩–፴፯)።

የጣቶችህን ሥራ ሰማዮችን አየሁ፣ መዝ. ፰፡፫። በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ፣ መዝ. ፴፫፡፮። አንተ የንጋት ልጅ እንዴት ከሰማይ ወደቅህ፣ ኢሳ. ፲፬፡፲፪ (፪ ኔፊ ፳፬፡፲፪)። ሰማያትም እንደ መጽሐፍ ጥቅልል ይጠቀለላሉ፣ ኢሳ. ፴፬፡፬። አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እፈጥራለሁ፣ ኢሳ. ፷፭፡፲፯። እግዚአብሔር የሰማይንም መስኮት ይከፍታል፣ ሚል. ፫፡፲።

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ስምህ ይቀደስ፣ ማቴ. ፮፡፱ (፫ ኔፊ ፲፫፡፱)። ጻውሎስ ወደ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ ተነጠቀ፣ ፪ ቆሮ. ፲፪፡፪። ዝምታ በሰማይ ሆነ፣ ራዕ. ፰፡፩ (ት. እና ቃ. ፹፰፡፯–፲፰)።

እስከ መጨረሻው በታማኝነት ከዘለቁ፣ ሰማይ ትቀበላቸዋለች፣ ሞዛያ ፪፡፴፭። በሰማይ ያለው የአባታችሁ ልጆች እንድትሆኑም ያደርጋልና፣ ፫ ኔፊ ፲፪፡፴፭።

በሰማይ ደመና እመጣለሁ፣ ት. እና ቃ. ፴፭፡፲፯። ኤልያስ ሞትን ሳይቀምስ ወደሰማይ ተወሰደ፣ ት. እና ቃ. ፲፲፡፲፫። የክህነት መብቶች እና የሰማይ ሀይሎች የማይነጣጠሉ ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፲፳፩፡፴፯። ሁለት አይነት የሰማይ ፍጥረቶች አሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፳፱፡፩።

ፅዮን ወደ ሰማይ ተወሰደች፣ ሙሴ ፯፡፳፫።

ሰቆቃመ ኤርምያስ

በኤርምያስ የተጻፈ የብሉይ ኪዳን መፅሐፍ። ግጥም ወይም ኢየሩሳሌም እና የእስራኤል ሀገር በወደቁበት ምክንያት የተጻፉ የሀዘን መዝሙሮች። መፅሐፉ የተጻፈው በ፭፻፸፯ ም.ዓ. አካባቢ ከተማዋ ከወደቀች በኋላ ነበር።

ሰባ። *ደግሞም ሐዋሪያ፤ የመልከ ጼዴቅ ክህነት ተመልከቱ*

በመልከ ጼዴቅ ክህነት ውስጥ ወንዶች ሊሾሙበት የሚችሉ ሀላፊነት። ዛሬ፣ የሰባ ቡድኖች የቤተክርስቲያኗ አጠቃላይ ባለስልጣኖች እና የክልል አመራሮች ናቸው። ሰባዎች በቀዳሚ አመራር እና በአስራ ሁለት ሐዋሪያት ቡድን አመራር ስር በጌታ ስም ያገለግላሉ (ት. እና ቃ. ፲፯፡፴፱)። ሙሉ ጊዜ አቸውን ለማስተማር ይሰጣሉ።

ከጌታ ሌሎቹን ሰብዓ ሾመ፣ ሉቃ. ፲፡፩።

ሰባዎቹ ወንጌልን እንዲሰብኩ፣ እና ልዩ የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክሮች እንዲሆኑ ተጠርተዋል፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፳፭–፳፯። ሰባዎች፣ በአስራ ሁለቱ አመራር በኩል ቤተክርስቲያኗን በመገንባት እና የእርሷን ጉዳዮች በሀገሮች ውስጥ ሁሉ በመቆጣጠር በጌታ ስም ሰሩ፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፴፱። ስራው የሚያስፈልገው ከሆነ ሌሎች ሰባዎች፣ እንዲሁን ሰባት ጊዜ ሰባ፣ ምረጥ፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፶፫–፶፯። የሰባዎች ቡድን የተመሰረተው የሚጓዙ ሽማግሌዎች በአለም ሁሉ ስለ ስሜ እንዲመሰክሩ ነው፣ ት. እና ቃ. ፲፳፱፡፲፴፯–፲፴፱።

ሰው፣ ሰዎች። *ደግሞም መንፈስ፤ ሴት፤ ሴቶች፤ እህት፤ እግዚአብሔር፤ አምላክ፤ ወንድሞች፤ ወንድም፤ የመንፈስ ፍጥረት፤ የእግዚአብሔር ወንድ እና ሴት ልጆች ተመልከቱ*

ስለሁሉም የሰው ዘር፣ ወንድ እና ሴቶች፣ የሚናገር ነው። ሁሉም ወንዶችና ሴቶች የሰማይ አባት የመንፈስ ልጆች ናቸው። በሚሞት ሰውነት ሲወለዱ፣ ስጋዊና ሟች ሰውነቶችን ተቀበሉ። እነዚህ ሰውነቶች የተፈጠሩት በእግዚአብሔር መልክ ነበር (ዘፍጥ. ፩፡፳፯–፳፯)። አስፈላጊ የሆኑትን ስነስርዓቶች ለመቀበል ብቁ የሆኑ ወንዶች እና ሴቶች፣ ቃል ኪዳኖችን በማክበር፣ እናም የእግዚአብሔር ትእዛ

ዛትን በማክበር ወደዘለአለማዊነታቸው ለመግባትና እንደ እግዚአብሔር ለመሆን ይችላሉ።

እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ ዘፍጥ. ፩፡፳፯ (ሞዛያ ፯፡፳፯፣ ት. እና ቃ. ፳፡፲፣–፲፰)። ታስበው ዘንድ ሰው ምንድር ነው፣ መዝ. ፰፡፬–፮። በሰው የሚታመን ሥጋ ለባሹንም ክንዱ የሚያደርግ ርጉም ነው፣ ኤር. ፲፯፡፭ (፪ ኔፊ ፱፡ ፡፡፡፣ ፳፰፡፳፯፣ ፳፯፣ ፡፡፩)።

ኅልማሳ ሆኜ ግን የልጅነትን ጠባይ ሽሬአለሁ፣ ፮ ቆሮ. ፲፫፡፲፩።

ሰዎች የሚኖሩትም ደስታም እንዲኖራቸው ዘንድ ነው፣ ፪ ኔፊ ፪፡፳፭። ፲፱ ተፈጥሮአዊው ሰው የእግዚአብሔር ጠላት ነው፣ ሞዛያ ፫፡፲፱። እናንተ ምን ዐይነት ሰዎች መሆን ይገባችኋል፣ ፫ ኔፊ ፳፯፡፳፯።

የሰው ስራ እንጂ የእግዚአብሔር ስራ አይሰናከልም፣ ት. እና ቃ. ፫፡፫። ሰውን ከእግዚአብሔር አስበልጠህ መፍራት አልነበረብህም፣ ት. እና ቃ. ፫፡፯ (ት. እና ቃ. ፡፡፡፣ ፲፳፪፡፱)። ሁሉም ነገሮች የተፈጠሩት ለሰው ጥቅም ነው፣ ት. እና ቃ. ፶፱፡፲፰።

ሰው ምንም እንዳልሆነ አወቅኩኝ፣ ሙሴ ፩፡፲። የእግዚአብሔር ስራና ክብር የሰውን ህያውነት እና ዘለአለማዊ ህይወት ማምጣት ነው፣ ሙሴ ፩፡ ፡፡፡።

ሰው፣ የሰማይ አባት የመንፈስ ልጅ፣ እነርሱም በግምባራቸው ወድቀው፣ አምላክ ሆይ፥ አንተ የሰው ሁሉ ነፍስ አምላክ ነህ አሉ፣ ዘኁል. ፲፮፡፳፪ (ዘኁል. ፳፯፡፲፮)። እናንተ የአምላካችሁ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ፣ ዘዳግ. ፲፬፡፩። አማልክት ናችሁ፥ ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ፣ መዝ. ፹፪፡፮። የሕያው አምላክ ልጆች ይባላሉ፣ ሆሴ. ፩፡፲። ለሁላችን አንድ አባት ያለን አይደለምን? አንድ አምላክስ የፈጠረን አይደለምን፣ ሚል. ፪፡፲።

የእግዚአብሔር ዘመዶች ነን፣ የሐዋ. ፲፯፡፳፱። የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን መንፈስ ይመስክራል፣ ሮሜ ፰፡፲፮። ለመናፍስት አባት ልንገዛ ተገባን፣ ዕብ. ፲፪፡፱።

የሰዎች መንፈስ ሁሉ ህይወትን ወደ ሰጣቸው ወደ እግዚአብሔር ይመለሳሉ፣ አልማ ፴፡፲፩።

የአለሞች ኗሪዎችም የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፷፯፡፳፱። ሰው ደግሞ በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር ጋር ነበር፣ ት. እና ቃ. ፶፫፡፳፫፣ ፳፱።

እግዚአብሔር አምላክም ከምድር ፊት በፍጥረታዊ አካል ከመፈጠራቸው በፊት በመንፈሳዊ አካል ፈጥሮአቸዋል፣ ሙሴ ፫፡፭–፯። እኔ እግዚአብሔር ነኝ፣ አለምንና ስጋ ከማግኘታቸው በፊት ሰዎችን የፈጠርኩኝ ነኝ፣ ሙሴ ፮፡፶፭።

የሰው እንደ እግዚአብሔር አይነት ለመ ሆን ያለው ችሎታ፣ እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ እናንተ ፍጹማን ሁኑ፣ ማቴ. ፭፡፴፰ (፫ ኔፊ ፲፪፡፴፰)። አማልክት ናችሁ አልሁ ተብሎ በሕጋችሁ የተጻፈ አይደለምን፣ ዮሐ. ፲፡፴፬ (ት. እና ቃ. ፷፮፡፶፰)። የእግዚአብሔር ወራሾች ነን ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን፣ ሮሜ ፰፡፲፯። ልጅ ነህ፣ ልጅም ከሆንህ ደግሞ በክርስቶስ የእግዚአብሔር ወራሽ ነህ፣ ገላ. ፬፡፯። ሲገለጥ፣ እርሱን እንመስላለን፣ ፩ ዮሐ. ፫፡፪። ድል ለነሣው ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ ይቀመጥ ዘንድ እሰጠዋለሁ፣ ራዕ. ፫፡፳፩።

ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሰጠ ኋቸው፣ ፫ ኔፊ ፩፡፲፯።

ሰለስቲያል መንግስትን የሚወርሱ አማልክቶች፣ እንዲሁም የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፷፮፡፹፣ ፹፰። ከእዚያም እነርሱም አምላኮች ይሆናሉ፣ ምክንያቱም ሀይል ስለሚኖራቸው፣ ት. እና ቃ. ፪፴፪፡፳።

ሰውነት። *ደግሞም ስጋዊ ሞት፣ ስጋዊ፣ የሚሞት፣ ትንሳኤ፣ ነፍስ ተመልከቱ*

በእግዚአብሔርም ምስል ተፈጥሮ ከመንፈስ ጋር በመጣመር ህያው ሰውን የሚሰራ ስጋዊ፣ የስጋና የአጥንት የሰውነት አካል። የወንድ እና ሴት ሰዎች አካላዊ ሰውነቶች በትንሳኤ ከመንፈሳቸው ጋር ለዘለአለም ተመልሰው ይጣመራሉ። ቅዱሣት መጻህፍት አብረው የተጣመሩትን ሰውነት እና መንፈስ እንደ ነፍስ ይጠሩታል (ዘፍጥ. ፪፡፯፣ ት. እና ቃ. ፹፯፡፲፭፣ ሙሴ ፫፡፯፣ ፬፣ ፲፬፣ አብር. ፭፡፯)።

እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፣ ዘፍጥ. ፪፡፯ (ሙሴ ፫፡፯)።

መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና እኔን ዳስሳችሁ እዩ፣ ሉቃ. ፳፬፡፴፱። ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ፣ ፩ ቆሮ. ፱፡፳፯። ፍጥረታዊ አካል አለ መንፈሳዊ አካል ደግሞ አለ፣ ፩ ቆሮ. ፲፭፡፴፩። ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ ነው፣ ያዕ. ፪፡፳፮።

የሚሞተው ሰውነት ወደ ማይሞተው ሰውነት ይነሳል፣ አልማ ፲፭፡፴፫–፴፭። ማንኛውም የሰውነት ክፍል ወደ ቀድሞው ይመለሳል፣ አልማ ፴፭፡፪። ኢየሱስ ከሞት የተነሳውን ሰውነቱን ለኔፋውያን አሳየ፣ ፫ ኔፊ ፲፡፲፭–፲፱፣ ፲፭፡፲፫–፲፭።

አብ እንደ ሰው ተጨባጭ የሆነ የስጋ እና አጥንቶች ሰውነት አለው፣ ወልድም ደግሞ እንዲሁ አለው፣ ት. እና ቃ. ፻፴፡፳፪።

እግዚአብሔር በእርሱ ሰውነት አምሳል ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው፣ ሙሴ ፮፡፱ (ዘፍጥ. ፱፡፮)።

ሰዎች። *ሰው፣ ሰዎች ተመልከቱ*

ሰይጣን። *ዲያብሎስ ተመልከቱ*

ሰዱቃውያን። ደግምም አይሁዶች ተመልከቱ

በአይሁዶች መካከል ትንሽ ነገር ግን በፖለቲካ ሀይለኛ የነበሩ ቡድን። ምናልባት በደንብ የሚታ ወቁበት ነገር የሙሴን ህግ በማይለወጥ አስተሳሰብ በቃላቱ በማመናቸው እና የመንፈሳትንና የመላእ ክትን እውነትነት እንዲሁም የትንሳኤን እና የዘ ለአለም ህይወት ትምህርቶችን በመካዳቸው ነበር (ማር. ፲፪፡፲፰–፳፯፤ የሐዋ. ፬፡፩–፮፣ ፳፫፡፯–፱)።

ሰዶም። ደግምም ገሞራ ተመልከቱ

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ በጌታ የተደመሰሰ ኃጢ ያተኛ ከተማ (ዘፍጥ. ፲፱፡፲፪–፳፱)።

ሲያል። ደግምም መንፈሳዊ ሞት፤ ኩነኔ፤ የጥፋት ልጆች፤ ዲያብሎስ ተመልከቱ

የኋለኛው ቀን ራዕይ ስለሲያል በሁለት አስተ ያየት አለው። መጀመሪያ፣ ይህ በሟችነት ትእ ዛዝ አክባሪ ያልሆኑት ለጊዜ የሚኖሩበት የመንፈስ አለም ነው። በዚህ አስተያየት፣ ሲያል መጨረሻ አለው። በእዚያ ያሉት መንፈሶች ወንጌሉን ይማ ራሉ፣ እናም ንስሀ ከገቡ በኋላም ብቁ ወደ ሆኑበት የክብር ደረጃ በትንሳኤ ይነሳሉ። ንስሀ የማይገቡት፣ ግን የጥፋት ልጆች ያልሆኑት፣ በአንድ ሺህ አመት በሙሉ በሲያል ይቆያሉ። ከእነዚህ አንድ ሺህ አመ ቶች ስቃይ በኋላ፣ ወደ ቲለስቲያል ክብር በትንሳኤ ይነሳሉ (ት. እና ቃ. ፹፯፡፴፯–፴፱፤ ፴፰፡፲–፲፩)።

ሁለተኛ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢያት ክፍያ ያልዳኑት በቋሚነት የሚኖሩበት ቦታ ነው። በዚህ አስተያየት፣ ሲያል ዘላቂ ነው። ይህም ለእነዚያ “ረክሰው ለቀሩት” ነው (ት. እና ቃ. ፴፰፡፴፫፣ ፲፪)። ይህም ሰይጣን፣ መላእክቱ፣ እና አብ ከገለ ጸው በኋላ ወልድን የካዱ የጥፋት ልጆች ለዘለአ ለም የሚኖሩበት ነው (ት. እና ቃ. ፹፯፡፴፣–፴፯)።

ቅዱሣት መጻህፍት አንዳንዴ ሲያልን እንደ ድቅ ድቅ ጨለማ ይገልጹታል።

የዳዊት ነፍስ በሲኦል አትተውም፣ መዝ. ፲፮፡፲ (መዝ. ፴፮፡፲፣)።

እሳቱም ወደማይጠፋበት ወደ ገሃነም ወደማይ ጠፋ እሳት ሂድ፣ ማር. ፱፡፵፣ (ሞዛያ ፪፡፴፯)። በሲኦልም በሥቃይ ሳለ አሻቅቦ አየ፣ ሉቃ. ፲፮፡፳፪–፳፫ (ት. እና ቃ. ፲፩፡፲፣)። ሞትና ሲኦ ልም በእነርሱ ዘንድ ያሉትን ሙታን ሰጡ፣ ራዕ. ፳፡፲፣።

የተዘጋጀ ቦታ፣ አዎን፣ እንዲሁም አሰቃቂው ገሀነም አለ፣ ፮ ኔፊ ፲፭፡፴፭። በስጋ ፈቃድ የዲ ያብሎስን መንፈስ ወደ ሲኦል እንዲወስደን ሀይል ይሰጠዋል፣ ፪ ኔፊ ፪፡፳፱። ክርስቶስ ከሞት እና ሲያል የምንድንበትን መንገድ አዘጋጅቷል፣ ፪ ኔፊ ፱፡፲–፲፪። ረክሰው የቀሩት ወደዘለአለም ስቃይ ይሄዳሉ፣ ፪ ኔፊ ፱፡፲፯። ዲያብሎስ ነፍሳቸውን እንዲህ ያታልላል፣ እናም በጥንቃቄ ወደ ሲኦል ይመራቸዋል፣ ፪ ኔፊ ፳፰፡፳፩። ኢየሱስ ነፍሴን ከሲኦል አድኗታል፣ ፪ ኔፊ ፴፫፡፯። ከሲያል ህመም ራሳችሁን ፍቱ፣ ያዕቆ. ፫፡፲፩። በዲያብሎስ ምርኮ መወሰድ፣ እናም እስከሚጠፉም በፈቃዱ መመራት የሲኦል ሰንሰለትም ማለት ነው፣ አልማ ፲፪፡፲፩። ክፉዎች ወደ ድቅድቅ ጨለማ እስከትንሳኤው ድረስ ይጣላሉ፣ አልማ ፴፣፡፲፣–፲፬። የረከሱት ከእግዚአ ብሔር ጋር መኖር በሲያል ከመኖር በላይ አሰቃቂ ነው፣ ሞር. ፱፡፭።

ከእጁ የሚሰጠው ቅጣት መጨረሻ የሌለው ቅጣት ነው፣ ት. እና ቃ. ፲፱፡፣–፲፪። ሲያል ለዲያብሎስ እና ለመላእክቱ የተዘጋጀ ቦታ ነው፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፴፯–፴፰። እግዚአብሔርን በእምነት የሚቀበሉ ከሞት እና ከሲያል ሰንሰለት ይድናሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፴፰፡፳፣፡፣

ሲድራቅ። ደግምም ዳንኤል ተመልከቱ

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ ሶስቱ የእስራኤል ወጣ ቶች ሲድራቅ፣ ሚሳቅ እና አብደናጎ ከዳንኤል ጋር ወደ ባቢሎን ንጉስ ናቡከደነፆር ቤተመንግስት የተ ወሰዱት ነበሩ። የሲድራቅ የእብራውያን ስም ሐና ንያ ነበር። አራቱ ወጣት ሰዎች ከንጉሱ ስጋና ወይን በመካፈል እራሳቸውን አንበክልም አሉ (ዳን. ፩)። ሲድራቅ፣ ሚሳቅ እና አብደናጎ ወደ እሳት እቶን ተወርውረው ነበር እናም በተአምራት ድነው ነበር (ዳን. ፫)።

ሲፓራ። ደግምም ሙሴ ተመልከቱ

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የሙሴ ባለቤት እና የዮቶር ሴት ልጅ (ዘፀአ. ፪፡፳፩፣ ፲፰፡፪)።

ሳሌም። ደግምም መልከ ጼዴቅ፤ ኢየሩሳሌም ተመልከቱ

በብሉይ ኪዳን ውስጥ መልከ ጼዴቅ የገዛት ከተማ። በዚህ ቀን በኢየሩሳሌም ቦታ ላይ የምትገኝ ይሆን ነበር። ሳሌም በእብራውያን ቋንቋ “ሰላም” ከሚለው ቃል ጋር የምትመሳሰል ነች።

የሳሌም ንጉሥ መልከ ጼዴቅም እንጀራንና የወ ይን ጠጅን አወጣ፣ ዘፍጥ. ፲፬፡፲፰።

የሳሌም ንጉሥና የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበር፣ ዕብ. ፯፡፩–፪።

መልከ ጼዴቅ የሳሌም ምድር ሁሉ ንጉስ ነበር፣ አልማ ፲፫፡፲፣–፲፰።

ሳሙኤል፣ የብሉይ ኪዳን ነቢይ

የሕልቃና እና የሐና ወንድ ልጅ፣ ሳሙኤል የተ ወለደው እንደ እናቱ የጸሎት መልስ ነበር (፩ ሳሙ. ፩)። በልጅነቱ በሴሎ ድንኳን ውስጥ ሊቀ ካህን በሆ ነው ዔሊ እንዲጠብቀው ተሰጠ (፩ ሳሙ. ፪፡፲፩፣ ፫፡፩)። ጌታ በወጣትነቱ ነቢይ እንዲሆን ጌታ

ጠራው (፩ ሳሙ. ፫)። ኤሊ ከሞተ በኋላ፣ ሳሙኤል ታናቅ ነቢይ እና የእስራኤል ዳኛ ሆነ እናም ህግን ስርዓር፣ እና ደንበኛ የሀይማኖት አምልኮን በምድር ውስጥ እንዲገኝ በዳግም መለሰ (፩ ሳሙ. ፬፥፲፭–፲፰፤ ፯፥፫–፲፯)።

፩ ሳሙ. ፳፰፥፫–፳ ሳሙኤል በሳዖል ጥያቄ ምክንያት የዓይንዶር መናፍስትን የምትጠራ አንዲትን ሴት ከሞት ያመጣበትን ታሪክ የያዘ ነው። ይህም ከእግዚአብሔር የመጣ ራይይም አልነበረም፣ ምክንያቱም መናፍስትን የምትጠራ ሴት ወይም ሌላ ከመናፍስት የሚናገሩት በነቢይ ላይ ተጽእኖ ኖሯቸው በእርሱ ወይም በእርሷ ጥያቄ ሊታይ አይችልም።

የ፩ እና ፪ ሳሙኤል መፅሐፎች፣ በአንዳንድ መፅሐፍ ቅዱሶች ውስጥ መፅሀፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ እና ካዕል አንድ መፅሀፍ ናቸው። በሌሎች ውስጥ ሁለት መፅሀፎች ናቸው። መፅሐፎቹ ከሳሙእል መወለድ እስከ ንጉስ ዳዊት መሞት በፊት ድረስ የ፻፴ አመታት ጊዜን የሚሸፍኑ ነበሩ።

መፅሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ፣ ምዕራፍ ፩–፫ ጌታ የኤሊ ቤተሰብን እንደረገመና እንደቀጣ እንዲሁም ሳሙኤል ሊቀ ካህን እና ዳኛ እንዲሆን እንደ ጠራ ይገልጻሉ። ምዕራፍ ፬–፯ የኪዳን ታቦት በፍልስጥኤም እጆች እንደወደቀ ይናገራሉ። ምዕራፍ ፯–፰ የሀሰት አማልክት እና ኃጢያተኛ ንጉስ መኖርና ሳሙኤል የሰጠውን ማስጠንቀቂያ ይመዘግባሉ። ምዕራፍ ፱–፲፭ የሳዖል መንግስት እና የንጉስነቱን ግዛት ይገልጻሉ። ምዕራፍ ፲፮–፴፩ የዳዊትን እና ሀይል ያገኘበትን ታሪክ ይነግራሉ—ሳሙኤል ጎልያድን የገደለውን ዳዊት ቀባ። ሳዖል ዳዊትን ጠላ፣ ነገር ግን ዳዊት ምንም እንኳን ይህን ለማድረግ እድል ቢኖረውም ሳዖልን ለመግደል ፈቃደኛ አለነበረም።

መፅሐፈ ሳሙኤል ካልዕ፣ ይህ መፅሐፍ የዳዊትን እንደ ይሁዳ እናም በመጨረሻ እንደ እስራኤል ሁሉ ንጉስ ዘመነ መንግስት የያዘ ነው። ምዕራፍ ፩–፬ በይሁዳ ከተዘወደ በኋላ፣ በዳዊት ተከታዮች እና በሳዖል ተከታዮች መካከል የነበረውን ትግል ያሳያሉ። ምዕራፍ ፭–፲ ዳዊት በብዙ ምድሮች ላይ ሁሉ ሀይለኛ እንደሆነ ያሳያሉ። ምዕራፍ ፲፩–፲፪ ዳዊት በኃጢያቶቹ እና በቤተሰቡ አመፅ ምክንያት መንፈሳዊ ጥንካሬው መዳከሙን ያሳያሉ። ምዕራፍ ፳፪–፳፬ ዳዊት ከጌታ ጋር ለመታረቅ የሞከረበትን ይገልጻሉ።

ሳም። *ደግሞም ሌሂ፣ የኔፊ አባት ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ የሌሂ ሶስተኛ ወንድ ልጅ (፩ ኔፊ ፪፥፭)። እርሱም ጌታን ለመከተል የመረጠ ጻድቅ እና ቅዱስ ሰው ነበር (፩ ኔፊ ፪፥፲፯፤ ፪ ኔፊ ፭፥፭–፯፤ አልማ ፫፥፮)።

ሳምራዊ። *ደግሞም ሰማርያ ተመልከቱ*

የሰሜን የእስራኤል መንግስት በአሶር ከተያዘች በኋላ በሰማርያ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ የመፅሐፍ ቅዱስ ህዝቦች። ሳምራዊዎች በክፍል አይሁዶች እናም በክፍል አህዛብ ነበሩ። ሀይማኖታቸውም የአይሁድ እና የጣዖት አምላኪ እምነትንና ስራን የሚከልስ ነበር። በሉቃ. ፲፥፳፭–፴፯ ውስጥ የሚገኘው የመልካሙ ሳምራዊ ምሳሌ ሳምራዊ የእስራኤላውያን ሀይማኖት ስለካዱ አይሁዶች ለሳምራዊን ስላላቸው ጥላቻ ያሳያል። ጌታ ሐዋሪያት ወንጌልን ለሳምራዊ እንዲያስተምሩ መመሪያ ሰጠ (የሐዋ. ፩፥፯–፰)። ፊልጶስ የክርስቶስ ወንጌልን ለሳምራዊ ህዝብ በውጤታማነት ሰበከ እናም በመካከላቸውም ብዙ ታዕምራቶችን አከናወነ (የሐዋ. ፰፥፭–፴፱)።

ሳራ። *ደግሞም አብርሐም ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የአብርሐም የመጀመሪያ ሚስት። እድሜዋ በገፋበት ጊዜ የይስሐቅ እናት ሆነች (ዘፍጥ. ፲፰፥፱–፲፭፤ ፳፩፥፪)።

ሳርያ። *ደግሞም ሌሂ፣ የኔፊ አባት ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ የሌሂ ባለቤት (፩ ኔፊ ፭፥፩–፰፤ ፰፥፲፬–፲፯፤ ፲፰፥፲፱) እና የላማን፣ ላሙኤል፣ ሳም፣ ኔፊ፣ ያዕቆብ፣ የዮሴፍ፣ እና የሴት ልጆች እናት (፩ ኔፊ ፪፥፭፤ ፪ ኔፊ ፭፥፯)።

ሳንሀድሪን። *ደግሞም አይሁዶች ተመልከቱ*

የአይሁድ የህግ መወሰኛ ምክር ቤት እና በህዝባዊ እና በሀይማኖታዊ ነገሮች ውስጥ የአይሁድ ታላቅ ፍርድ ቤት። ሳንሀድሪን ከዋና ካህናት፣ ጸሀፊዎች፣ እና ሽማግሌዎች መካከል የተመረጡ ሰባ አንድ አባላት ያለው ነው። በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ፣ ይህም ሸንጎ ተብሎ ይጠራል (ማቴ. ፳፯፥፶፱፤ ማር. ፲፬፥፶፭፤ የሐዋ. ፭፥፴፬)።

ሳዖል፣ የእስራኤል ንጉስ

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ ከመከፋፈሏ በፊት የእስራኤል የመጀመሪያ ንጉስ። ምንም እንኳን በግዛቱ መጀምሪያ ላይ ጻድቅ ቢሆንም፣ በኋላም በትዕቢት ተሞላ እና በእግዚአብሔር ታዛዥ የማይሆን ነበረ (፩ ሳሙ. ፱–፴፩)።

ሴም። *ደግሞም ኖኅ፣ የመፅሐፍ ቅዱስ የአባቶች አለቃ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የኖኅ ጻድቅ ወንድ ልጅ እና፣ በባህል መሰረት፣ አረብ፣ ዕብራውያን፣ ባቢሎናውያን፣ አሶር፣ እና ፎኒሲያውያን አባል የሆኑባቸው የሴማውያን ወይም የሴም ህዝብ ቅድም አባት (ዘፍጥ. ፭፥፳፱–፴፪፤ ፯፥፲፤ ፯፥፲፫፤ ፱፥፳፯፤ ፲፥፳፩–፴፪፤ ሙሴ ፰፥፲፪)። በኋለኛው ቀን ራዕይ

ውስጥ ሴም “ታላቁ ሊቀ ካህን” ተብሎ ተጠቁሟል (ት. እና ቃ. ፗ፴፯፡ፗ፩)።

ሴት። *ደግሞም አዳም ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የአዳምና የሔዋን ጻድቅ ወንድ ልጅ።

ሴት ፍጹም ሰው ስለነበረ፣ እና በምሳሌ መል ኩም እንደ አባቱ መልክ ነበር፣ ት. እና ቃ. ፗ፲፯፡ፗ፪–ፗ፲ (ዘፍጥ. ፭፡፫)። በመንፈስ አለም ውስጥ፣ ሴት ከሀይለኞቹ አንዱ ነበር፣ ት. እና ቃ. ፗ፴፯፡ፗ።

እግዚአብሔር እራሱን ለሴት ገለጸ፣ ሙሴ ፤፡፩–፲፣ ፯–፲፱።

ሴት፣ ሴቶች። *ደግሞም ሰው፣ ሰዎች፤ እህት፤ ወንድሞች፣ ወንድም ተመልከቱ*

የእግዚአብሔር ሴት ልጅ የሆነች ጎልማሳ ሴት። ሴትን አንዳንድ ጊዜ በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ እንደ ክብር ርዕስ ይጠቀሙበታል (ዮሐ. ፲፱፡፳፤ አልማ ፲፱፡፲)።

እግዚአብሔርም ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራ ቸው፣ ዘፍጥ. ፩፡፳፯ (ሙሴ ፪፡፳፯፤ ፤፡፱፣ አብር. ፬፡፳፯)። የምግባረ ጥሩ ሴት ዋጋ ከቀይ ዕንቁ በላይ ታላቅ ነው፣ ምሳ. ፴፩፡፲–፴፩።

ሴት የወንድ ክብር ናት፣ ፩ ቆሮ. ፲፩፡፯። ነገር ግን በጌታ ዘንድ ሴት ያለ ወንድ ወንድም ያለ ሴት አይሆንም፣ ፩ ቆሮ. ፲፩፡፲፩። ሴቶች በሚገባ ልብስ ሰውነታቸውን ይሸልሙ፣ ፩ ጢሞ. ፪፡፱–፲።

እኔ ጌታ እግዚአብሔር በሴቶች ንፅህና እደሰታ ለሁ፣ ያዕቆ. ፪፡፳፯፡፳።

ኃጢያትሽ ተሰርዮልሻል፣ እናም አንቺ የተመር ጥሽ ሴት ነሽ፣ ት. እና ቃ. ፳፭፡፲። ሴቶች፣ በባሎ ቻቸው የመደገፍ መብት አላቸው፣ ት. እና ቃ. ፲፲፡፪።

ሴዴቅያስ። *ደግሞም ሙሌቅ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የይሁዳ የመጨረሻ ንጉስ (፪ ነገሥ. ፳፬፡፲፯–፳፣ ፳፭፡፪–፯)። ሴዴቅያስ ነቢዩ ኤርምያስን አሰረ (ኤር. ፴፪፡፩–፭)፣ እናም ኤር ምያስ ስለሴዴቅያስ በምርኮ መያዝ ተነበየ (ኤር. ፴፬፡፪–፳፣ ፳፭)። ሄሂ እና ቤተሰቡ በሴዴቅያስ ዘመነ መንግስት የመጀመሪያ አመት ጊዜ በኢየ ሩሳሌም ውስጥ ይኖሩ ነበር (፩ ኔፊ ፩፡፱)። ከአ ንዱ በስተቀር ሁሉም የሴዴቅያስ ልጆች ተገድለው ነበር፣ ልጁ ሙሌቅ ወደ ምዕራብ ክፍለ አለም አመ ለጠ (ኤር. ፶፪፡፲፣ ኦምኒ ፩፡፲፩፣ ሔሌ. ፲፡፳፩)።

ስህተት። *በደል ተመልከቱ*

ስልጣን። *ደግሞም ሀይል፣ መሾም፣ ሹመት፣ ክህነት፣ የክህነት ቁልፎች፣ ጥሪ፣ በእግዚአብሔር መጠራት፣ የተጠራበት ተመልከቱ*

የእግዚአብሔር ስራን ለማከናወን በምድር ላይ ለእግዚአብሔር አብ ወይም ለኢየሱስ ክርስቶስ እና በስማቸው ለመስራት ለተጠሩት ወይም ለተሾሙት ሰዎች የተሰጠ ፈቃድ።

ልኬሀለሁ፣ ዘፀአ. ፫፡፲፪–፲፭። ያዘዝሁህን ነገር ሁሉ አንተ ትነግረዋለህ፣ ዘፀአ. ፯፡፪።

አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርቱን ሥልጣን ሰጣ ቸው፣ ማቴ. ፲፡፩። እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እና ንተ አልመረጣችሁኝም፣ እና ሾምኋችሁ፣ ዮሐ. ፲፭፡፲፮።

ኔፊና ሌሒ በታላቅ ኃይልና ስልጣን ሰበኩ፣ ሔሌ. ፭፡፲፤ የሔሌመን ወንድ ልጅ ኔፊ የእግዚአብሔር ሰው፣ ታላቅ ኃይልና ስልጣን ከእግዚአብሔር የተ ሰጠው ነበር፣ ሔሌ. ፲፩፡፲፤ (፫ ኔፊ ፯፡፲፯)። ኢየ ሱስ ለአስራ ሁለቱ ኔፋውያን ሀይልና ስልጣን ሰጣ ቸው፣ ፫ ኔፊ ፲፪፡፩–፪።

ጆሴፍ ስሚዝ በእግዚአብሔር ተጠርቶና ተሹሞ ነበር፣ ት. እና ቃ. ፳፡፪። ካልተሾመ፣ እና ስልጣን እንዳለው በቤተክርስቲያኗ የሚታወቅ ካልሆነ በስ ተቀር፣ ለማንም ወንጌሌን እንዲሰብክ ወይም ቤተ ክርስቲያኔን እንዲገንባ አይሰጠውም፣ ት. እና ቃ. ፴፪፡፲፩። ሽማግሌዎች በስልጣን እየሰሩ ወንጌሉን ይስበኩ፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፳። የመልከ ጼዴቅ ክህነት በመንፈሳዊ ነገሮች ለማስተዳደር ስልጣን አለው፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፳፣ ፲፯–፲፱። በመለኮ ታዊ ስልጣን የተደረገው ህግ ይሆናል፣ ት. እና ቃ. ፲፳፡፳፡፱።

የሚሰብክ ወይም ለእግዚአብሔር የሚያገለግል ስልጣን ባላቸው በእግዚአብሔር መጠራት አለ በት፣ ኢ.ኢ. ፩፡፭።

ስሚዝ፣ ሀይረም። *ደግሞም ስሚዝ፣ ጆሴፍ ዳግማዊ ተመልከቱ*

የጆሴፍ ስሚዝ ታላቅ ወንድም እና ታማኝ ጓደኛ። በየካቲት ፱፣ ፲፰፻፱ (እ.አ.አ.) ተወልዶ ነበር። የቤ ተክርስቲያኗ ሁለተኛ ፓትሪያርክ ከመሆን በተ ጨማሪ፣ እርሱ በቤተክርስቲያኗ አመራር ውስጥ እንደ ጆሴፍ ረዳት አገለገለ። በሰኔ ፳፯፣ ፲፰፻፴፬ (እ.አ.አ.)፣ በካርቴጅ እስር ቤት ውስጥ ከጆሴፍ ጋር ሰማዕት ሆነ።

እግዚአብሔር ለሀይረም በወንድሙ ጆሴፍ በኩል መመሪያዎች ገለጸለት፣ ት. እና ቃ. ፲፩፣ ፳፫፡፫። አገልጋዬ ሀይረም ስሚዝ በልቡ ቅንነት የተባረከ ነው፣ ት. እና ቃ. ፲፳፬፡፲፭። ሀይረም የቤ ተክርስቲያኗን የፓትሪያርክ ሀላፊነትን እንዲወስድ ታዛዛ፣ ት. እና ቃ. ፲፳፬፡፲፩–፲፯፣ ፲፳፭። ጆሴፍ እና ሀይረም በካርቴጅ እስር ቤት ውስጥ ሰማዕት ሆኑ፣ ት. እና ቃ. ፲፱፡፳። ሀይረም እና ሌሎች ምርጥ መን

ፈሶች በዘመን ሙላት እንዲመጡ ተጠብቀው ነበር፣ ት. እና ቃ. ፲፴፯፡፶፫።

ስሚዝ፣ ሉሲ ማክ። *ደግሞም* ስሚዝ፣ ጆሴፍ ቀዳማዊ፤ ስሚዝ፣ ጆሴፍ ዳግማዊ *ተመልከቱ*

የነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ እናት እና የጆሴፍ ስሚዝ ቀዳማዊ ባለቤት (ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፬፡፬፣ ፣ ፳)። የተ ወለዱት በሐምሌ ፳፣ ፲፯፻፳፯ (እ.አ.አ.) ነበር እናም በግንቦት ፭፣ ፲፰፻፶፯ (እ.አ.አ.) ሞቱ።

ጆሴፍ እናቱን በራዕይ በሰለስቲያል መንግስት ውስጥ አየ፣ ት. እና ቃ. ፲፴፯፡፭።

ስሚዝ፣ ሳሙኤል ኤች። *ደግሞም* ስሚዝ፣ ጆሴፍ ዳግማዊ *ተመልከቱ*

የነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ ታናሽ ወንድም (ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፬)። ሳሙኤል የተወለደው በ፲፰፻፷ (እ.አ.አ.) ነበር እናም በ፲፰፻፸፬ (እ.አ.አ.) ሞተ። ከመፅሐፈ ሞርሞን ስምንት ምስክሮች አንዱ ነብር እናም በዳ ግም ለተመለሰችው ቤተክርስቲያን ውስጥም እንደ መጀመሪያው ሚስዮን አገለገለ (ት. እና ቃ. ፭፣ ፡፪፣ ፡፲፪፡፡፲፭፣ ፡፲፮፡፡፲–፲፣ ፡፲፭፡፡፲፣ ፡፲፮፡፡፲–፲፣ ፡፲፰፡፡፲)።

ስሚዝ፣ ኤማ ሄል። *ደግሞም* ስሚዝ፣ ጆሴፍ ዳግማዊ *ተመልከቱ*

የነብዩ የጆሴፍ ስሚዝ ባለቤት። ጌታ ለቤተክ ርስቲያኗ መዝሙር እንድትመርጥኤማን አዘዛት። እርሷም እንደ የሴቶች መረዳጃ ማህበር የመጀመ ሪያ ፕሬዘደንት አገለገለች።

ጌታ ለኤማ ስሚዝ ያለውን ፍላጎት ራዕይ ተሰ ጥቶ ነበር፣ ት. እና ቃ. ፭፭፡፡ ጌታ ኤማ ስሚዝን ጋብቻን በሚመለከት ምክር ሰጣት፣ ት. እና ቃ. ፲፴፪፡፡፲፩–፲፲፮፡፡

ስሚዝ፣ ጆሴፍ ቀዳማዊ። *ደግሞም* ስሚዝ፣ ሉሲ ማክ፣ ስሚዝ፣ ጆሴፍ ዳግማዊ *ተመልከቱ*

የነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ አባት። በሐምሌ ፲፪፣ ፲፯፻፳፭ (እ.አ.አ.) የተወለዱ ነበሩ። ሉሲ ማክን አገቡ፣ እናም እነርሱም ዘጠኝ ልጆች ወለዱ (ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፬)። ጆሴፍ በ፯ላኛው ቀን ዳግም መመለስ ታማኝ ሰው እና የቤተክርስቲያኗ የመጀ መሪያ ፓትሪያርክ ሆኑ። በመስከረም ፲፬፣ ፲፰፻፶ (እ.አ.አ.) ሞቱ።

እግዚአብሔር በልጁ ጆሴፍ በኩል መመሪያ ሰጠው፣ ት. እና ቃ. ፬፣ ፭፲፣ ፭። የሚሸመግለው አገልጋዩ፣ አሁን በሚኖርበት ቦታ ከቤተሰቡ ጋር ይቀጥል፣ ት. እና ቃ. ፣ ፭። የሚሸመግለው አገል ጋዩ ጆሴፍ ከአብርሐም ጋር በቀኝ እጁ በኩል ተቀ ጥሞ ጧል፣ ት. እና ቃ. ፲፭፬፡፡፲፬። ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ አባቱን በራዕይ በሰለስቲያል መንግስት ውስጥ አየ፣ ት. እና ቃ. ፲፴፯፡፭።

መላእኩ ወደ አባቱ በመሄድ ስለመጀመሪያው ራዕይ እንዲነግረው ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊን አዘዘ፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፶፬–፶፡

ስሚዝ፣ ጆሴፍ ኤፍ

የቤተክርስቲያኗ ስድስተኛ ፕሬዘደንት፣ የሀይረም እና የሜሪ ፊልዲንግ ስሚዝ ብቸኛ ወንድ ልጅ። የተወለዱት በህዳር ፲፫፣ ፲፰፻፴፭ (እ.አ.አ.) ነበር እና በህዳር ፲፱፣ ፲፱፻፲፰ (እ.አ.አ.) ሞቱ።

ጆሴፍ ኤፍ ስሚዝ የሙታን ደህንነትን ራዕይ ተቀበሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፴፯፡፡

ስሚዝ፣ ጆሴፍ ዳግማዊ። *ደግሞም* መፅሐፈ ሞርሞን፤ ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች፤ የመጀመሪያው ራዕይ፤ የታላቅ ዋጋ ዕንቁ፤ የወንጌል ዳግም መመለስ፤ የጆሴፍ ስሚዝ ትርጉም (ጆ.ስ.ት.) *ተመልከቱ*

የኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ ቤተክርስቲያንን በምድር ላይ በዳግም ለመመለስ የተመረጠ ነቢይ። ጆሴፍ ስሚዝ በዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ በቨርሞንት ስቴት ውስጥ ተወለደ እናም ከ፲፰፻፭ እስከ ፲፰፻፸፬ (እ.አ.አ.) ድረስ በህይወት ኖረ።

በ፲፰፻፳ (እ.አ.አ.)፣ እግዚአብሔር አብ እና ኢየ ሱስ ክርስቶስ በጆሴፍ ታዩ፣ እናም በምድር ካሉት ቤተክርስቲያኖች መካከል ማንኛቸውም እውነተኛ እንዳልሆኑ ተማረ (ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፩–፳)። በኋላም በአሜሪካ ክፍለ አህጉር ላይ ይኖሩ የነበሩ የጥንት ህዝቦችን መዝገብ የያዘውን የወርቅ ሰሌዳ የተደ በቀበትን ቦታ በገለጸለት በመልአክ ሞሮኒ ተነበኝ (ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፳፱–፴፪)።

ጆሴፍ የወርቅ ሰሌዳዎችን ተረጎመ እናም በ፲፰፻፴ (እ.አ.አ.) እንደ መፅሐፈ ሞርሞን አተማ ቸው (ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፳፯–፳፱፣ ፫፳)። በ፲፰፻፳፱ (እ.አ.አ.)፣ ክህነትን ከመጥምቁ ዮሐንስ፣ እናም ከጴጥሮስ፣ ከያዕቆብ፣ እና ከዮሐንስ ተቀበሉ። (ት. እና ቃ. ፲፫፣ ፳፯፡፡፲፪፣ ፲፳፯፡፡፳፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፳፡፳–፫)።

በእግዚአብሔር እንደተመራም፣ በሚያዝያ ፮፣ ፲፰፻፴ (እ.አ.አ.) ጆሴፍ እና ብዙ ሌሎች ዳግም የተ መለሰችውን የኢየሱስ ክርቶስ ቤተክርስቲያን አደ ራጁ። (ት. እና ቃ. ፳፡፩–፪)። በጆሴፍ አመራር፣ በካናዳ፣ በእንግሊዝ፣ እና በዮናይትር ስቴትስ በም ስራቅ ክፍሎች፣ በልዩም በኦሀዮ፣ በምዙሪ፣ እናም በኢሊኖይ ውስጥ፣ ቤተክርስቲያኗ አደገች። ጠን ካራ መሳደድ ጆሴፍን እና ቅዱሳንን የትም በሚ ሰፍሩበት ቦታዎች ሁሉ ተከተሏቸው። በሰኔ ፳፯፣ ፲፰፻፴፪ (እ.አ.አ.)፣ ጆሴፍ እና ወንድሙ ሀይረም በካርቴጅ ኢሊኖይ፣ በዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜ ሪካ ውስጥ ሰማዕት ሆኑ።

የያዕቆብ ልጅ ጆሴፍ ስለ ጆሴፍ ስሚዝ ተነበየ፣ ፪ ኔፊ ፫፡፭–፲፭።

ጌታ በምድር ነዎሪዎች ላይ የሚመጣውን መቅሰፍት በማወቁ፣ ጌታ አገልጋዩን ጆሴፍ ስሚዝን ጠራ፣ ት. እና ቃ. ፩፡፲፯ (ት. እና ቃ. ፲፱፡፲፫)። ጆሴፍ ስሚዝ የዚህ ቤተክርስቲያን መጀመሪያ ሽማግሌና የኢየሱስ ክርስቶስ ሀዋሪያ እንዲሆን ተሾመ፣ ት. እና ቃ. ፭፡፪። ጆሴፍ ሐዋሪያ እንዲሆን በጴጥሮስ፣ እና እብያእቆብ፣ እና በዮሃንስ ተሾመ፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፲፪። ጆሴድ እና ስድኒ ሪግደን የአብ አንድያ ልጅ እንዳዩ መሰከሩ፣ ት. እና ቃ. ፷፯፡፳፫። ከኦሊቨር ካውደሪ ጋር፣ ጆሴፍ ስሚዝ ጌታን በራዕይ አየ፣ ት. እና ቃ. ፲፣፡፩–፱። ጌታ ጆሴፍን አስተዳዳሪ ሽማግሌ፣ ተርጓሚ፣ ገላጭ፣ ባለ ራዕይ፣ እና ነቢይ እንዲሆን ጠራው፣ ት. እና ቃ. ፲፳፱፡፲፳፭። ጆሴፍ ስሚዝ፣ ከኢየሱስ በስተቀር፣ በዚህ አለም ውስጥ ለሰዎች ደህንነት ከኖሩ ሌሎች ሰዎች ሁሉ በላይ አድርጓል፣ ት. እና ቃ. ፲፱፡፲፭–፲፡

በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የመጡ ቅዱሣት መጻህፍት፣ ጆሴፍ በመልአክ ሞሮኒ የተሰጡትን የወርቅ ሰሌዳዎችን ክፍል ተረጎመ፣ ይህም ትርጉም በ፲፰፻፴ (እ.አ.አ.) እንደ መፅሐፈ ሞርሞን ታተመ። መሰረታዊ ትምህርቶችን እና የቤተክርስቲያኗን ድርጅቶች ዋና ሀሳቦችን የሚሰጡ ብዙ ራዕዮችንም ከጌታ ተቀበለ። ከእነዚህ ራዕዮች ብዙዎቹ አሁን ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች ተብለው በሚታወቁት ውስጥ ተካለሱ። የሙሴ፣ የአብር ሐም፣ እና የማቴዎች የተነሳሱ ትርጉሞችን፣ ከእራሱ ታሪክና ምስክሮች ክፍሎችን፣ እና የቤተክርስቲያኗን ትምህርት እና እምነት የያዙ አስራ ሶስት መረጃዎችን የያዘውን የታላቅ ዋጋ ዕንቁንም የማምጣት ሀላፊ የሆነ ነበር።

ስሜታዊ፣ ስሜታዊነት። *ደግምም ማመንዘር፣ ምኞት፣ በወሲብ የስነ ምግባር ጉድለት፣ ንጹህነት፣ ዝሙት መፈጸም ተመልከቱ*

ሳድቅ ላልሆነ የሰውነት ደስታን፣ በልዩም የወሲብ የስነ ምግባር ጉድለትን፣ ማፍቀር ወይም መውደድ።

የጌታው ሚስት በዮሴፍ ላይ ዓይንዋን ጣለች፣ ዘፍጥ. ፴፱፡፯።

ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል፣ ማቴ. ፭፡፳፰ (፫ ኔፊ ፲፪፡፳፰)። ነፍስን ከሚዋጋ ሥጋዊ ምኞት ራቁ፣ ፩ ጴጥ. ፪፡፲፩። የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ከአባት አይደሉም፣ ፩ ዮሐ. ፪፡፲፮።

በዓይንህ ምኞት ከእንግዲህ እንዳትጓዝ፣ **አልማ** ፴፱፡፱።

ቅዱስ ህጎችን በመተላለፍ ሰዎች ስጋዊ ሆኑ፣ ት. እና ቃ. ፳፡፳። ማንም በልባቸው ካመነዘሩ፣ መንፈስም አይኖራቸውም፣ ት. እና ቃ. ፳፫፡፲፮። ከፍተኛ ፍላጎታችሁን ሁሉ አቁሙ፣ ት. እና ቃ. ፹፰፡፪–፭።

ሰዎችም ስጋዊ፣ ስሜታዊና ዲያብሎሳዊ መሆን ጀመሩ፣ **ሙሴ** ፭፡፲፫ (ሞዛያ ፲፮፡፫፣ ሙሴ ፮፡፴፱)።

ስሜት። *ደግምም መንፈስ ቅዱስ ተመልከቱ*

የመንፈስ መነሳሻን መሰማት።

እናንተ ደንዝዛችኋል፣ ስለዚህ ቃሉ ሊሰማችሁ አልቻለም፣ ፩ ኔፊ ፲፯፡፴፭። ይህ ዕድገት በልባችሁ ውስጥ ሲሰማችሁ፣ በውስጣችሁ እንዲህ ማለት ትጀምራላችሁ፣ **አልማ** ፴፪፡፳፰።

ትክክል እንደሆነ ይሰማሃል፣ ት. እና ቃ. ፱፡፰። በጌታ ቤት መግቢያ በር ላይ የሚገቡት ህዝቦች ሁሉ ሀይልህ ይሰማቸው፣ ት. እና ቃ. ፲፱፡፲፫።

ስምዖን። *ደግምም እስራኤል፣ ያዕቆብ፣ የይስሐቅ ልጅ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የያዕቆብ እና የልያ ሁለተኛ ወንድ ልጅ (ዘፍጥ. ፳፱፡፴፣ ፴፭፡፳፣ ዘፀአ. ፩፡፪)። ሴኬማውያንን በመግደል ከሌዋ ጋር ተባበረ (ዘፍጥ. ፴፬፡፳፭–፴፩)። በዘፍጥረት ፴፱፡፩–፲ ውስጥ ስምዖንን በተመለከተ የያዕቆብ ትንቢት ይገኛል።

የስምዖን ጎሳ፣ የስምዖን ትውልዶች በብዙ ጊዜ ከይሁዳ ጎሳ ጋር በይሁድ መንግስት ድንበር ውስጥ ይኖሩ ነበር (ኢያ. ፲፱፡፩–፱፣ ፩ ዜና ፬፡፳–፴፫)። የስምዖን ጎሳ ከይሁዳ ጋር በመተባበር ከከነዓናውያን ጋር ተዋጉ (መሳ. ፩፡፫፣ ፲፯)። በኋላም የዳዊት ሰራዊት አባል ሆኑ (፩ ዜና ፲፪፡፳፭)።

ስምዖን ጴጥሮስ። *ጴጥሮስ ተመልከቱ*

ስራ ሰልቺ፣ ስራ ፈቺ

ሰነፍ እና በጽድቅ ስራዎች የማይሳተፍ።

ሊሠራ የማይወድ አይብላ፣ ፪ ተሰ. ፫፡፲።

እነርሱም ሰነፍ፣ በተንኮል የረቀቁ ህዝቦች ሆኑ፣ ፪ ኔፊ ፭፡፳፬። ከስራ ፈትነት ራስህን ቆጥብ፣ **አልማ** ፴፰፡፲፪።

ያለስራ የሚቀመጥ የሰራተኞችን እንጀራ አይበላም፣ ት. እና ቃ. ፴፪፡፴፪። በእጆቻችሁ የማትሰሩት ድሀ ሰዎችም ወዮላችሁ፣ ት. እና ቃ. ፶፯፡፲፯። ጥሩ ስራን በጉጉት አከናውኑ፣ ት. እና ቃ. ፶፰፡፳፯። ስራ ፈት መሆንን አቁሙ፣ ት. እና ቃ. ፹፰፡፲፭–፱።

ስራዎች

ጥሩም ይሁን መጥፎ፣ ሰው የሚፈጽመው። እያንዳንዱ ሰው በእራሱ ስራ ይፈረድበታል።

ጌታ ለሰው ሁሉ እንደ ሥራው ይመልስለታል፣ **ምሳ.** ፳፬፡፲፪።

መልካሙን ሥራችሁን እንዲያዩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ፣ **ማቴ.** ፭፡፲፮ (ቮ ኔፊ ፲፪፡፲፯)። በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ ወደ መንግስተ ሰማይ ይገባል፣ **ማቴ.** ፯፡፳፩። ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው፣ **ያዕ.** ፪፡፲፰–፳፮።

በስራዎቻቸው ሊፈረድባቸው ይገባል፣ **ፎ ኔፊ** ፲፭፡፴፪ (ሞዛያ ፫፡፳፬)። በጸጋ የምንድነው የምንችለውን ካደረግን በኋላ እንደሆነ እናውቃለን፣ **ፎ ኔፊ** ፳፭፡፳፫። ለመልካም ስራ በጭራሽ እንዳ ይታክቱ አስተምሯቸው፣ **አልማ** ፴፯፡፴፰። ሰዎች እንደስራቸው እንዲፈረድባቸው አስፈላጊ ነው፣ **አልማ** ፵፭፡፫። በሥራዎቻቸው ታውቁአቸዋላ ችሁ፣ **ሞሮኒ** ፯፡፭ (ት. እና ቃ. ፲፳፡፴፳)።

እኔ ጌታ ሁሉንም ሰዎች በስራዎቻቸው መሰረት እፈርድባቸዋለሁ፣ **ት. እና ቃ.** ፲፴፯፡፱።

ስነስርዓቶች። *ደግምም ለሙታን ደህንነት፣ ማተም፣ ማስተሳሰር፣ ቤተመቅደስ፣ የጌታ ቤት፣ የትውልድ ሐረግ፣ ደህንነት ተመልከቱ*

ቅዱስ ስርዓቶች። ስነስርዓቶች መንፈሳዊ ትር ጉም ያላቸው ስራዎችን የያዘ ነው። ደግሞም ስነ ስርዓቶች የእግዚአብሔር ህግጋት ማለት ናቸው።

በቤተክርስቲያና ውስጥ የሚከናወኑ ስነስርዓቶች የታመሙትን ማስታመም (ያዕ. ፭፡፲፬–፲፭)፣ ቅዱስ ቁርባንን መባረክ (ት. እና ቃ. ፳፡፷፯፣ ፷፱)፣ በማ ጥለቅ መጠመቅ (ማቴ. ፫፡፲፮፤ ት. እና ቃ. ፳፡፷፡፷፪–፷፬)፣ ልጆችን መባረክ (ት. እና ቃ. ፳፡፷)፣ መን ፈስ ቅዱስን መስጠት (ት. እና ቃ. ፳፡፳፳፤ ፴፫፡፲፭)፣ ክህነትን መስጠት (ት. እና ቃ. ፹፬፡፯–፲፯፤ ፻፯፡፻፴፭–፻፴)፣ የቤተመቅደስ ስነስርዓቶችን (ት. እና ቃ. ፻፳፬፡፴፴)፣ እና በአዲስና ዘለአለ ማዊ ቃል ኪዳን መጋባት (ት. እና ቃ. ፻፴፪፡፲፱–፳)ናቸው።

ሥርዓቱንም ሕጉንም አስተምራቸው፣ **ዘፀአ.** ፲፰፡፲፳። በትእዛዜም ይሄዱ ዘንድ ፍርዴንም ይጠ ብቁ፣ **ሕዝ.** ፲፭፡፲፱።

ህዝቡ የእግዚአብሔርን ስርዓቶች ለመፈፀም የሚተጉ ነበሩ፣ **አልማ** ፴፡፫። ስርአቶቹን በመ ጠበቅ በመራመድ ምን ይረባናል፣ ፫ **ኔፊ** ፳፯፡፲፫–፲፰።

የሚጸልየው፣ መንፈሱ የተዋረደውም፣ የእኔን ስነ ስርዓት ካከበረ፣ እርሱም በእኔ ተቀባይ ነው፣ **ት. እና ቃ.** ፶፪፡፲፰–፲፱።

የወንጌሉን ህግጋትና ስነ ስርዓቶችን በማክበር፣ የሰው ዘሮች ሁሉ መዳን ይችላሉ፣ **እ.አ.** ፭፡፫።

የወኪል ስነስርዓት፣ ለሞተ ሰው በወኪልነት በሚኖር ሰው የሚከናወን የሀይማኖት ስነስርዓት። እነዚህ ስነስርዓቶች ውጤት የሚኖራቸው ስነስርዓ ቶች የተከናወኑላቸው ሰዎች ከተቀበሉት፣ ከእነዚህ ጋር የተያያዙትን ቃል ኪዳኖች ከጠበቁ፣ በቅዱስ የተሰፋ መንፈስ ከተሳሰሩ በኋላ ብቻ ነው። እንደ ዚህ አይነት ስነስርዓቶች ዛሬ የሚከናወኑት በቤተ መቅደሶች ውስጥ ነው።

ስለ ሙታን የሚጠመቁ ምን ያደርጋሉ? ሙታንስ ከቶ የማይነሡ ከሆነ፣ ፩ **ቆሮ.** ፲፭፡፳፱።

ለሙታን መጠመቅ በቤተመቅደስ ውስጥ ይከና ወን፣ **ት. እና ቃ.** ፻፳፰፡፳፱–፴፤። ነፍሶች ለኃጢ ያት ስርየት በወኪል ስለመጠመቅ በመንፈስ አለም ውስጥ ተማሩ፣ **ት. እና ቃ.** ፻፴፯፡፳፱–፴፪።

ስጋ። *ደግምም ሰውነት፣ ስጋዊ፣ ስጋዊ፣ የሚሞት፣ ፍጥረታዊ ሰው ተመልከቱ*

ስጋ የተለያዩ ትርጉሞች አሉት፡ (፩) የሰው ዘርን፣ የእንስሳትን፣ የወፎችን፣ ወይም የአሳዎችን ሰውነቶች የሚሸፍን የሰውነት መሰሪያ፣ (፪) ሟች ነት፣ ወይም (፫) ስጋዊ የፍጥረታዊ ሰው።

የሰውነት መሰሪያ፣ ሕይወት ያለው ተንቀሳቃሽ ሁሉ መብል ይሁናችሁ፣ **ዘፍጥ.** ፱፡፫። አስፈላጊ ሳይሆን እንስሳት አይገደሉ፣ **ጆ.ስ.ት.** ዘፍጥ. ፱፡፲–፲፩ (ት. እና ቃ. ፵፱፡፳፩)።

እንስሳትን እና ወፎችን ለሰው ምግብ እና ለልብስ የሚጠቀምባቸው ናቸው፣ **ት. እና ቃ.** ፵፱፡፲፳–፲፱ (ት. እና ቃ. ፶፱፡፲፯–፳)። ስጋን በቁጠባ እንጠቀም ባቸው፣ **ት. እና ቃ.** ፹፱፡፲፪–፲፭።

ሟችነት፣ ኢየሱስ ወደ ሟችነት የተወለደው የአብ አንድያ ልጅ ብቻ ነው፣ **ዮሐ.** ፩፡፲፩ (ሞዛያ ፲፭፡፩–፫)።

አዳም የመጀመሪያም ስጋ ሆነ፣ **ሙሴ** ፫፡፯።

ስጋዊ ፍጥረታዊ ሰው፣ ሥጋ ለባሹንም ክንዱ የሚያደርግ ሰው ርኑም ነው፣ **ኤር.** ፲፯፡፭።

መንፈስ ተዘጋጅታለች፣ ሥጋ ግን ደካማ ነው፣ **ማር.** ፲፡፡ ፴፰ ። የሥጋ ምኞት ከአባት አይደለም፣ ፩ **ዮሐ.** ፪፡፲፮።

ኔፊ በስጋውና በኃጢያቶች ምክንያት አዘነ፣ **ፎ ኔፊ** ፡ ፡ ፲፯–፲፰፣ ፴፡ ከዲያብሎስና ከስጋ ፈቃ ድጋር አታስታርቁ፣ **ፎ ኔፊ** ፲፡፳፡ ።

ስጋ፣ ስጋዊነት። *ስሜታዊ፣ ስሜታዊነት ተመልከቱ*

ስጋዊ። *ደግምም ስሜታዊ፣ ስሜታዊነት፣ የአዳም እና የሔዋን ውድቀት፣ ፍጥረታዊ ሰው ተመልከቱ*

መንፈሳዊ ያልሆኑ አንዳንድ ነገሮች፣ በልዩም ይህ ቃል ስጋዊ ወይም ጊዜአዊ (ት. እና ቃ. ፳፯፡፲) ወይም አለማዊ፣ ስጋዊ፣ እና ስሜታዊ ለማለት ይጠ ቀምበታል (ሞዛያ ፲፯፡፲–፲፱)።

ስለዓለም ማሰብ ሞት ነው፣ ፤ ኤፊ ፤፡፡ ዲያብሎስ ቀስ ብሎም ወደ ስጋዊ ደህንነት ያባብላቸዋል፣ ፤ ኤፊ ፡፡ እራሳቸውን በስጋቸው ሁኔታ ተመለከቱ፣ ሞዛያ ፡፡ ፤ በስጋዊ ተፈጥሮው የቆየ ወድቆ ይቀራል፣ ሞዛያ ፡፡ ሁሉም ከእግዚአብሔር በመወለድ፣ ከስጋዊና ከወደቁበት ሁኔታ ይቀየራሉ፣ ሞዛያ ፡፡ ሰዎች ስጋዊ፣ ስሜታዊ፣ እናም ዲያብሎሳዊ ናቸው፣ አልማ ፡፡ ፤ ስጋን እና የራሱን ፍቃድ የሚከተለው መውደቅ አለበት፣ ት. እና ቃ. ፡፡ ሰው በስጋዊ አዕምሮው እግዚአብሔርን ማየት አይችልም፣ ት. እና ቃ. ፡፡ ፤ ሰዎችም ስጋዊ፣ ስሜታዊና ዲያብሎሳዊ መሆን ጀመሩ፣ ሙሴ ፡፡ ፤ ፡፡ ሮሜ ፡፡ ፤ ሮሜ ፡፡ ፤ ስጋዊ ሞት፣ ደግሞም ስጋዊ፣ የሚሞት፣ ትንሳኤ፣ የአዳም እና የሔዋን ውድቀት፣ ደህንነት ተመልከቱ

የሰውነት ከመንፈስ መለየት። ውድቀት ሟች ነትንና በምድርም ሞትን አመጣ (ፍ ኤፊ ፤ ፡፡ ሙሴ ፡፡ ፤ ፡፡)። የኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢያት ክፍያ ሁሉም ሰው ከሞት እንዲነሱ ዘንድ ሞትን አሸነፈ (ፍ ቆሮ. ፡፡ ፤ ፡፡–ፍ ፡፡)። ትንሳኤ በዚህ ህይወት ጥሩ ወይም መጥፎ ቢያደርጉም ለሁሉም ሰዎች የተሰጠ የነጻ ስጦታ ነው (አልማ ፡፡ ፤ ፡፡–ሮሜ ፡፡)። ከሞት ከተ ነሳን በኋላ ሰውነቶቻችን እንደገና መሞት ስለማይ ችሉ፣ እያንዳንዱ ሰው ስጋዊ ሞት የሚኖረው አንዴ ብቻ ነው (አልማ ፡፡ ፤ ፡፡)።

ሥጋ ለባሽ ሁሉ በአንድነት ይጠፋል ሰውም ወደ አፈር ይመለሳል፣ ኢዮብ ፡፡ ፤ ፡፡ የቅዱሳኑ ሞት በእግዚአብሔር ፊት የከበረ ነው፣ መዝ. ፡፡ ፤ ፡፡ አፈርም ወደ ነበረበት ምድር ይመለሳል፣ ነፍስም ወደ ሰጠው ወደ እግዚአብሔር ይመለሳል፣ መክ. ፡፡ ፤ ፡፡

ሞት በሰው በኩል መጣ፣ ፍ ቆሮ. ፡፡ ፤ ፡፡ አዳኝ የሞትና የሲኦል መክፈቻን ይዟል፣ ራዕ. ፡፡ ፤ ፡፡ ሞትም ኀዘንም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፣ ራዕ. ፡፡ ፤ ፡፡

ሞት በሰው ልጆች ላይ መጣ፣ ፤ ኤፊ ፡፡ ፤ ፡፡ (አልማ ፡፡ ፤ ፡፡)። ሞትን በፍርሃት ደረጃ በጭራሽ አልተመለከቱም፣ አልማ ፡፡ ፤ ፡፡ አልማ በሞ ትና በትንሳኤ መካከል ስላለው ሁኔታ ገለጸ፣ አልማ ፡፡ ፤ ፡፡

በእኔ የሚሞቱት ሞትን አይቀምሱም፣ ት. እና ቃ. ፡፡ ፤ ፡፡ ለሞት የተመደቡት አይ ፈውሱም፣ ት. እና ቃ. ፡፡ ፤ ፡፡ እስከሞትም ድረስ በሁሉም ነገር እፈትናችኋለሁ፣ ት. እና ቃ. ፡፡ ፤ ፡፡

ወደ አፈር ትመለሳለህ፣ ሙሴ ፡፡ ፤ ፡፡ አዳም ወደቀ፣ በውድቀቱም ሞት መጣ፣ ሙሴ ፡፡ ፤ ፡፡ ስጋዊ፣ የሚሞት፣ ደግሞም ሰውነት፣ ስጋዊ ሞት፣ አለም፣ የአዳም እና የሔዋን ውድቀት ተመልከቱ

ከመወለድ እስከ ስጋዊ ሞት ድረስ ያለ ጊዜ። ይህም አንዳንድ ጊዜ ሁለተኛው ሁኔታ ተብሎ ይጠራል።

ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ፣ ዘፍጥ. ፡፡ ፤ ፡፡–፡፡ (ሙሴ ፡፡ ፤ ፡፡–፡፡)። ነፍስ ወደ እግዚ አብሔር ይመለሳል እናም ሰውነትም አፈርም ወደ ነበረበት ምድር ይመለሳል፣ መክ. ፡፡ ፤ ፡፡ (ዘፍጥ. ፡፡ ፤ ፡፡ ሙሴ ፡፡ ፤ ፡፡)።

በሚሞት ሥጋችሁ ኃጢአት አይንገሥ፣ ሮሜ ፡፡ ፤ ፡፡ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ይለብ ሳል፣ ፍ ቆሮ. ፡፡ ፤ ፡፡ (ኢኖስ ፡፡ ፤ ፡፡ ሞዛያ ፡፡ ፤ ፡፡ ሞር. ፡፡ ፤ ፡፡)።

የሰው ዘመን የሙከራ ጊዜ ሆነ፣ ፤ ኤፊ ፡፡ ፤ ፡፡ (አልማ ፡፡ ፤ ፡፡ ፡፡ ፤ ፡፡)። ሰዎች እንዲኖሩ፣ አዳም ወደቀ፣ ፤ ኤፊ ፡፡ ፤ ፡፡ ይህ ሟቹ ሰው ነት የማይሞት በመሆን እንደሚነሳ ትመለከታላ ችሁን፣ አልማ ፡፡ ፤ ፡፡ ይህ ጊዜ እግዚአብሔ ርን ለመገናኘት የዝግጅት ወቅት ነው፣ አልማ ፡፡ ፤ ፡፡

እስከሞትም አትፍሩ፣ በዚህ አለም ደስታችሁ ሙሉ አይደለምና፣ ት. እና ቃ. ፡፡ ፤ ፡፡

ሁለተኛ ሁኔታቸውን የጠበቁትም ግርማ ይጨ መርላቸዋል፣ ኦብር. ፡፡ ፤ ፡፡

ስጦታ። ደግሞም የመንፈስ ስጦታዎች፣ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ተመልከቱ

እግዚአብሔር ብዙ በረከቶችና ስጦታዎች ለሰው ይሰጣል።

ብዙ መንፈሳዊ ስጦታዎች አሉ፣ ፍ ቆሮ. ፡፡ ፤ ፡፡ የሚበልጠውን የጸጋ ስጦታ በብርቱ ፈልጉ፣ ፍ ቆሮ. ፡፡ ፤ ፡፡ በጎ ስጦታ ሁሉ ፍጹምም በረ ከት ሁሉ ከእግዚአብሔር ናቸው፣ ያዕ. ፡፡ ፤ ፡፡

የመንፈስ ቅዱስ ኃይል የእግዚአብሔር ስጦታ ነው፣ ፍ ኤፊ ፡፡ ፤ ፡፡ ስጦታዎች የሉም የሚሉት የክርስቶስ ወንጌልን አያውቁም፣ ሞር. ፡፡ ፤ ፡፡ ሁሉም ጥሩ ስጦታዎች ከክርስቶስ ይመጣሉ፣ ሞሮኒ ፡፡ ፤ ፡፡–፡፡

ከእግዚአብሔር ስጦታዎች ሁሉ ታላቅ ስጦታ የሆነውን ዘላለማዊ ህይወት ነው፣ ት. እና ቃ. ፡፡ ፤ ፡፡ (ፍ ኤፊ ፡፡ ፤ ፡፡)። ስጦታዎች እግዚአብሔ ርን ለሚያፈቅሩት ይሰጣል፣ ት. እና ቃ. ፡፡ ፤ ፡፡ ሁሉም እያንዳንዱ ስጦታ አልተሰጣቸውም፣ ት. እና ቃ. ፡፡ ፤ ፡፡–ፍ ፡፡

ሶምሶን

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ ከእስራኤል “መሳፍንት” አስራሁለተኛው። በታላቅ የሰውነት ጥንካሬው የታ

ሶስቱ ኔፋውያን ደቀ መዛሙርቶች ፮፪

ወቀ ነበር፣ ነገር ግን ባደረጋቸው አንዳንድ ስነምግ ባራዊ ምርጫዎች እና ስራዎች ጥበባዊ አልነበረም (መሳ. ፲፫፡ ፳፬–፲፯፡ ፴፩)።

ሶስቱ ኔፋውያን ደቀ መዛሙርቶች። *ደግምም ኔፋውያን፣ የተቀየሩ ሰዎች፣ ደቀ መዛሙርት ተመልከቱ*

በምመሐፈ ሞርሞን ውስጥ የተጠቀሱት ክር ስቶስ ከመረጣቸው የኔፋውያን ደቀ መዛሙርት ሶስቱ።

ጌታ ለእነዚህ ደቀ መዛሙርቶች ጌታ እንደገና እስከሚመጣ ድረስ ወደ ክርስቶስ ነፍሳትን በማም ጣት በምድር ላይ እንዲቀሩ ለተወዳጁ ዮሐንስ የተ ሰጠውን አንድ አይነት በረከት ሰጣቸው። ምንም ስቃይ እንዳይሰማቸው እና እንዳይሞቱ ተቀይረው ነበር (፫ ኔፊ ፳፰፡)።

እስከሚመጣ ድረስ እንዲቆዩ ዘንድ ክርስቶስ የሶስቱ ደቀ መዛሙርቶችን ፍላጎት ፈቀደ፣ ፫ ኔፊ ፳፰፡ ፭–፱። የሞት ስቃይ በጭራሽ አይደርስባቸ ውም፣ ፫ ኔፊ ፳፰፡ ፮–፱። ደስታቸው ሙሉ ይሆ ናል፣ ፫ ኔፊ ፳፰፡ ፲። ለጊዜ ወደ ሰማይ ተነጥቀው ነበር፣ ፫ ኔፊ ፳፰፡ ፲፫–፲፯። ህዝቡን አስተማሩ እናም ብዙ ስደትንም ተፅናኑ፣ ፫ ኔፊ ፳፰፡ ፲፰–፳፫። ሞርሞንን አስተማር፣ ፫ ኔፊ ፳፰፡ ፳፬–፳፯ (ሞር. ፡ ፣–፲፩)። አህዛብን፣ አይሁዶችን፣ የተበ ተኑ ነሳዎችን፣ እና ሁሉንም ሀገሮች ያስተምራሉ፣ ፫ ኔፊ ፳፰፡ ፳፯–፳፱። ሰይጣን በእነርሱ ላይ ስልጣን አይኖረውም፣ ፫ ኔፊ ፳፰፡ ፴፱።

ሶፍንያስ

በኢዮስያስ ዘመነ መንግስት ጊዜ የኖረ የብሉይ ኪዳን ነቢይ።

ትንቢተ ሶፍንያስ፣ ምዕራፍ ፩ በቁጣ እና በችግር ስለሚሞላው ስለሚመጣው ቀን ይናገራል። ምዕራፍ ፪ የእስራኤል ህዝቦች ጽድቅን እና የዋህነትን እንዲ ፈልጉ ያበረታታል። ምዕራፍ ፫ ሁሉም ሀገሮች ለጠ ርነት ስለሚሰለፉበት ስለዳግም ምፅዓት ይናገራል። ጌታ፣ ግን፣ በመካከላቸው ይነግሳል።

ሺብሎን። *ደግምም አልማ፣ የአልማ ወንድ ልጅ ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ የዳግማዊ አልማ ልጅ። ሺብሎን ወንጌልን ለዞራግማውያን አስተ ማረ እናም ለጻድቅነቱም ተሰደደ። በታማኝነቱ እና በትእግስቱ ምክንያት ጌታ ከሚሳደድበት አዳነው (አልማ ፴፰)። ሺብሎን ለጥቂት ጊዜም የኔፋውያን መዝገቦችን ጠበቀ፣ (አልማ ፳፫፡ ፭–፪፣ ፲፭–፲፫)።

ሺዝ። *ደግምም ያሬዳውያን ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ የያሬዳውያን የወታ ደሮች መሪ። የያሬዳውያን ሀገርን በሙሉ ባጠፋው ታላቅ ጦርነት መጨረሻ ላይ ሞተ (ኤተር ፲፡ ፲፣ ፲፭–፲፭፡ ፴፭)።

ሼረም። *ደግምም የክርስቶስ ተቃዋሚ ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ ክርስቶስን የካደ እናም ምልክትን በግድ የፈለገ ሰው (ያዕቆ. ፯፡ ፭–፰)።

ሽማግሌ። *ደግምም ክህነት፣ የመልከ ጼዴቅ ክህነት ተመልከቱ*

ሽማግሌ የሚባለው ቃል በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለያዩ መንገዶች ተጠቅመውበታል። በብሉይ ኪዳን ውስጥ በብዙ ጊዜ በጎሳ ውስጥ የሚገኙትን፣ በመንግስት ጉዳዮች የሚመኩበትን፣ ሽማግሌዎች ይጠቅሣል (ዘፍጥ. ፱፡ ፯፣ ኢያ. ፳፡ ፬፣ ሩት ፬፡ ፪፣ ማቴ. ፲፭፡ ፪)። እድሜአቸው እና አጋጣሚያቸው የእነርሱን ምክር ታላቅ ዋጋ ይሰጠዋል። ቦታቸ ውም የክህነት ጥሪ መሆኑ አስፈላጊም አልነበረም።

በብሉይ ኪዳን ጊዜዎች በመልከ ጼዴቅ ክህነት ውስጥ የተሾሙ ሽማግሌዎችም ነበሩ (ዘፀአ. ፳፬፡ ፱–፲፩)። በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ ሽማግሌዎች በቤተክ ርስቲያኗ ውስጥ እንደ ክህነት ሀላፊነቶች ተጠቅሰ ዋል (ያዕ. ፭፡ ፲፬–፲፭)። በኔፋውያን መካከል በክህ ነት ስልጣን ውስጥ እንደ ሽማግሌዎች የተሾሙም ነበሩ (አልማ ፬፡ ፯፣ ፲፯፣ ሞሮኒ ፫፡ ፭)። በዚህ ዘመን ውስጥ፣ ጆሴፍ ስሚዝ እና ኦሊቨር ካውደሪ የተ ሾሙ የመጀመሪያ ሽማግሌዎች ነበሩ (ት. እና ቃ. ፳፡ ፪–፫)።

ሽማግሌ አሁን የመልከ ጼዴቅ ክህነት ባለስልጣን ለሆኑት ሁሉ የተሰጠ ስም ነው። ለምሳሌ፣ ወንድ ሚስዮኖች እንደ ሽማግሌዎች ነው የሚጠሩት። ደግ ሞም፣ ሐዋሪያ ሽማግሌ ነው፣ የአስራ ሁለቱ ሐዋሪ ያት ቡድን አባላትን ወይም የሰባዎች ቡድን አባላ ትን በዚህ ርዕስ መናገር ትክክለኛ ነው (ት. እና ቃ. ፳፡ ፴፯፣ ፭ ጴጥ. ፭፡ ፭)። በአሁን ቤተክርስቲያኗ ውስጥ የተሾሙ ሽማግሌዎች ሀላፊነቶች በኋለኛው ቀን ራዕይ ተሰጥተዋል (ት. እና ቃ. ፳፡ ፴፯–፴፭፣ ፴፪፡ ፴፬፣ ፴፮፡ ፪፣ ፲፯፡ ፲፪)።

ሙሴም ለእስራኤልም ሽማግሌዎች ሁሉ ጻፈ፣ ዘዳግ. ፴፭፡ ፱።

በርናባስ ወደ ሽማግሌዎቹ እርዳታ ሰደደ፣ የሐዋ. ፲፭፡ ፴። በየቤተክርስቲያኑም ሽማግሌዎች ተሾሙ፣ የሐዋ. ፲፡ ፳፫ (ቲቶ ፩፡ ፭)። ሽማግ ሌዎች በታመሙት ላይ እንዲጸልዩ የተጠሩበት፣ ያዕ. ፭፡ ፲፡

እጁን በመጫን ሽማግሌዎች ሾመ፣ **አልማ** ፯፡ ፩።

ሽማግሌዎቹም ልጆችን ይባርኳቸው፣ ት. እና ቃ. ፳፡ ፷። ሽማግሌዎች ስብሰባዎችን በመ

ንፈስ ቅዱስ አመራር ያካሂዱ፣ ት. እና ቃ. ፯፮፡፪። ሽማግሌዎች መጋቢነታቸውን መግለጫ ይስጡ፣ ት. እና ቃ. ፫፪፪፡፭። ሽማግሌዎች ወንጌልን ለሀገሮች ይስበኩ፣ ት. እና ቃ. ፲፬፲፫፡፯።

ሽማግሌው አልማ

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ በክፉው ንጉስ ኖህ ቀናት ቤተክርስያኗን ያደራጀ የኔፋውያን ነቢይ።

የክፉው ኖህ ካህን እና የኔፊ ትውልድ ነበር፣ ሞዛያ ፲፯፡፭–፪። አቢናዲን ካዳመጠ እና ካመነ በኋላ፣ በንጉሱ ተሰደደ። ሸሽ፣ ተደበቀ፣ እና የአቢናዲን ቃላት ጻፈ፣ ሞዛያ ፲፯፡፲–፲፱። ንስሀ ገባ እና የአቢናዲን ቃላት አስተማረ፣ ሞዛያ ፲፯፡፩። በምርሞን ውሀዎች ውስጥ ጠመቀ፣ ሞዛያ ፲፯፡፲፪–፲፮። ቤተክርስትያኗን አደራጀ፣ ሞዛያ ፲፯፡፲፯–፳፩። ከህዝቦቹ ጋር ወደ ዛራሕምላ ደረሰ፣ ሞዛያ ፳፩፡፳፭። በቤተክርስትያኗ ላይ ስልጣን ተሰጠው፣ ሞዛያ ፳፮፡፡ ፈረደም ቤተክርስትያኗንም መራ፣ ሞዛያ ፳፮፡፡ ፴፬–፴፱። በልጁ ላይ የሊቀ ካህን ሀላፊነትን አረጋገጠ፣ አልማ ፩፡፩ (ሞዛያ ፳፱፡፴፪፣ አልማ ፭፡፣)።

ሽንገላ (ውሸት)፣ መዋሸት፣ ማታለል። *ደግምም ሐሰት፣ ተንኮል ተመልከቱ*

በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ፣ ማታለል ማለት አንድን ሰው እውነት ባልሆነ ነገር እንዲያምን ማድረግ ነው።

ለባልንጀራውም በሽንገላ ያልማለ ወደ እግዚአብሔር ተራራ ይወጣል፣ መዝ. ፳፬፡፣ ፫–፬። ከሸንጋይ አድነኝ፣ መዝ. ፴፣፡፭። ክፉውን መልካም መልካሙን ክፉ ለሚሉ ወዮላቸው፣ ኢሳ. ፭፡፳ (፪ ኔፊ ፲፭፡፳)።

ማንም ራሱን አያታልል፣ ፩ ቆሮ. ፣፡፣፲፰። ማንም በከንቱ ንግግር አያታልላችሁ፣ ኤፌ. ፭፡፮። ክፉ ሰዎች ያታልላሉም ይታለላሉም፣ ፪ ጢሞ. ፣፡፣፣። ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው ሰይጣን ተጣለ፣ ራዕ. ፲፪፡፱። ሀገሮችን እንዳያታልል ዘንድ ሰይጣን ይያዛል፣ ራዕ. ፳፡፭–፣፡፡

ጌታ ሊታለል አይችልም፣ ፪ ኔፊ ፱፡፴፩። በእግዚአብሔር ፊት ባለማስመሰል ወልድን ብትከተሉ መንፈስ ቅዱስን ትቀበላላችሁ፣ ፪ ኔፊ ፴፩፡፣፣፡። ሼረም በዲያብሎስ ሀይል እንደተታለለ ተናዘዘ፣ ያዕቆ. ፯፡፣፣። የንጉስ ኖህ ህዝቦች በድለላ ቃላት ተታልለው ነበር፣ ሞዛያ ፣፣፩፡፯።

ጥበባኛው መንፈስ ቅዱስን እንደ መሪው ወስዷል፣ እናም አልተታለለም፣ ት. እና ቃ. ፴፭፡፴፯። አታላይ ለሆኑት ወዮላቸው፣ ት. እና ቃ. ፴፡፯።

ለማታለል እና እንዳያዩ ለማድረግ፣ ሰይጣን፣ የውሸት አባት ሆነ፣ ሙሴ ፬፡፬።

ቀስተ ዳመና። *ደግምም መርከብ፣ ኖኅ፣ የመፅሐፍ ቅዱስ የአባቶች አለቃ፣ የኖኅ ዘመን የጥፋት ውሀ ተመልከቱ*

የእግዚአብሔር ከኖህ ጋር የገባው ቃል ኪዳን ምልክት (ዘፍጥ. ፱፡፣፣–፣፣)። ጆ.ስ.ት.፣ ዘፍጥረት ፱፡፴፩–፴፭ (ተጨማሪ) ቃል ኪዳኑ ምድር እንደገና በጥፋት ውሀ እንዳማትሸፈን፣ የሔኖክ ፅዮን እን ደምትመለስ፣ እና ጌታ በምድር ለመኖር እንደገና እንደሚመጣ የተስፋ ቃላትን በተጨማሪ ይሰጣል።

ቀራንዮም። *ጎልጎታ ተመልከቱ*

ቀራጭ። *ደግምም የሮሜ ግዛት ተመልከቱ*

በጥንት ሮሜ፣ ለመንግስት ቀረጥ የሚሰበስብ ሰው። ቀራጮች በአይሁዶች በአጠቃላይ የተጠሉ ነበሩ። አንዳንድ ቀራጮች ወንጌሉን ወዲያው ተቀበሉ (ማቴ. ፱፡፡ ፱–፣፣ ሉቃ. ፣፱፡፡–፳)።

ቀንበር። *ደግምም ደቀ መዛሙርት ተመልከቱ*

በእንስሳት ወይም በሰዎች አንገት ላይ አብረው እንዲተሳሰሩ የሚያደርጋቸው እቃ። የክርስቶስ ቀንበር የደቀ መዛሙርት ምሳሌ ነው፣ ነገር ግን የባርነት ቀንበር የመጨቆን ምሳሌ ነው።

ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነው፣ ማቴ. ፣፩፡፴፩–፴። ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ፣ ፪ ቆሮ. ፮፡፣፣፡። በባርነት ቀንበር አት ያዙ፣ ገላ. ፭፡፩።

ማናችሁንም በባርነት ቀንበር ስር እንድናመጣ ችሁ አንፈልግም፣ አልማ ፴፩፡፪።

የቅዱሳን ስቃይ የብረት ቀንበር፣ ይህም ጠንካራ ማስረያ፣ የሲኦል ሰንሰለቶች ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፲፳፣፡፩–፣፡ ፣–፳።

ቀኖና። *ደግምም መፅሐፈ ሞርሞን፣ መፅሐፍ ቅዱስ፣ ቅዱሳት መጻህፍት፣ ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች፣ የታላቅ ዋጋ ዕንቁ ተመልከቱ*

የታወቀ፣ ስልጣናዊ የቅዱሣት መጻህፍት ስብስብ። በኋለኛው ቀን ቅዱሳን በኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስትያን ውስጥ፣ የቀኖና መፅሐፎች ከብሉይ እና ከአዲስ ኪዳን መጻህፍቶች፣ ከመፅሐፈ ሞርሞን፣ ከትምህርት እና ቃል ኪዳኖች፣ እና ከታላቅ ዋጋ ዕንቁ በተጨማሪ ይፉ የሆኑ ስራዎች ተብለው ይጠራሉ።

ቀያፋ። *ደግምም ሐና፣ ሊቀ ካህኑ፣ ሰዱቃውያን ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ ሊቀ ካህን እና የሐና አማች። ቀያፋ ኢየሱስን እና ደቀ መዛሙርቱን በመቃወም ተሳታፊ ነበር (ማቴ. ፳፮፡፣–፣፡፣ ዮሐ. ፣፩፡፴፯–፴፩፣ ፣፲፡፡–፣፣)።

ቀይ ባህር። *ደግሞም ሙሴ ተመልከቱ*

በግብፅ እና በአረብ መካከል የሚገኝ ውሀ። የእ ዚህ ሁለት የሰሜን ባህረ ሰሌጣዎች የሲና ባህር ዳርን ይሰራሉ። እስራኤላውያን በሙሴ አመ ራር በኩል በደረቅ መሬት ላይ እንዲያልፉ ጌታ በተአምራት ቀይ ባህርን ከፈለ (ዘፀአ. ፲፬፡፲፫–፴፭፣ ዕብ. ፲፩፡፳፱፤ ፡ ፡). ባህሩ በሙሴ እንደተከ ፈለ በኋለኛው ቀን ራዕይ ተረጋግጧል (፩ ኔፊ ፡ ፡ ፣ ሔለ. ፰፡፲፩፣ ት. እና ቃ. ፰፡፲፣ ሙሴ ፩፡፳፭)።

ቀዳሚ አመራር። *ደግሞም ራዕይ፣ የክህነት ቁልፎች፣ ፕሬዘደንት ተመልከቱ*

የቤተክርስቲያኗ ፕሬዘደንትና አማካሪዎቹ እነርሱ ቤተክርስቲያኗን በሙሉ የሚመሩ የሶስት ሊቀ ካህ ናት ቡድን ናቸው። ቀዳሚ አመራር የክህነት ቁል ፎችን በሙሉ ይዘዋል።

የመንግስት ቁልፎች ሁልጊዜም የሊቀ ካህን አመ ራር ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፲፩፡፪። የሊቀ ካህናት አመራር በሁሉም ሀላፊነቶች የማስተዳደር መብት አላቸው፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፱፣ ፳፪። ቃሌን የሚ ቀበል ማንኛውም የቀዳሚ አመራርን ይቀበላል፣ ት. እና ቃ. ፲፲፪፡፳፣ ፴። ቀዳሚ አመራር ለቤተ ክርስቲያኗ የእግዚአብሔርን ቃላት (ራዕዮች) ይቀ በላሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፳፩፡፲፳፯።

ቀድሞ መመረጥ። *ደግሞም ቅድመ ምድራዊ ህይወት ተመልከቱ*

እግዚአብሔር የኃያል የመንፈስ ልጆቹ በስጋዊ ህይወታቸው አንዳንድ ሚስዮኖችን እንዲያሟሉ በቅድመ ምድር አስቀድሞ መምረጡ።

እግዚአብሔር የአሕዛብን ድንበር አቆመ፣ ዘዳግ. ፴፪፡፰። በሆድ ሳልሠራህ ነቢይ አድርጌሃለሁ፣ ኤር. ፩፡፭።

እግዚአብሔር የተወሰኑትን ዘመኖች መደበላ ቸው፣ የሐዋ. ፲፯፡፳፮። አስቀድሞ ያወቃቸው፣ አስቀድሞ ደግሞ ወስኖአል፣ ሮሜ ፰፡፳፱–፴። ዓለም ሳይፈጠር በፊቱ እንሆን ዘንድ መረጠን፣ ኤፌ. ፩፡፫–፬። ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝ እንዲ ሆን ቀድሞ ተመርጧል፣ ፩ ጴጥ. ፩፡፲፱–፳ (ራዕ. ፲፫፡፰)።

ከአለም መመስረት በፊት ተጠርተውና ተዘጋጅ ተው ነበር፣ አልማ ፲፫፡፩–፱።

ተመረጡት በተከበሩትና በታላቆቹ መካከል እን ደነበሩም አየሁ፣ ት. እና ቃ. ፲፴፰፡፹፭–፹፯።

ከመጀመሪያ ጊዜ ጀምሮ የተመረጠው ተወዳጁ ልጄ፣ ሙሴ ፬፡፪። አብርሐም ከመወለዱ በፊት ተመርጦ ነበር፣ አብር. ፫፡፳፫።

ቁርባን። *በኩራት ተመልከቱ*

ቁጣ። *ደግሞም መጥላት፣ ጥላቻ፣ ፍቅር ተመልከቱ*

ቁጣ የግልፍተኝነት ስሜት የምታይበት ነው። ጌታ ቅዱሳን ቁጣቸውን እንዲቆጣጠሩ አስጠ ነቀቃቸው (ማቴ. ፭፡፳፪)። ወላጅ ወይም ልጅ ሌሎች ቤተሰብን ማጎሳቆል አይገባቸውም። (፪ ኔፊ ፲፭፡፳፫፣ ት. እና ቃ. ፩፡፲፫)

ቃየንም እጅግ ተናደደ ፊቱም ጠቆረ፣ ዘፍጥ. ፬፡፭። እግዚአብሔር ከቍጣ የራቀ፣ እና ምሕረ ቱም ብዙ ነው መዝሙረ ዳዊት፣ መዝ. ፻፴፭፡፰። የለዘበች መልስ ቍጣን ትመልሳለች፣ ምሳ. ፲፭፡፩። ቍጡ ሰው ጠብን ያነሣሣል፣ ትዕግሥተኛ ሰው ግን ጸጥ ያሰኘዋል፣ ምሳ. ፲፭፡፲፰ (ምሳ. ፲፬፡፳፱)። ስለ ስሜ ቍጣዬን አዘገያለሁ፣ ኢሳ. ፵፰፡፱። ዘወትር ወደሚያስቆጡኝ ህዝቦች እጆቼን ዘረጋሁ፣ ኢሳ. ፷፭፡፪–፫።

ቀኝ ጉንጭህን በጥፊ ለሚመታህ ሁሉ ሁለተኛ ውን ደግሞ አዙርለት፣ ማቴ. ፭፡፴፱። እናንተም አባቶች ሆይ፥ ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና በተግሣጽ አሳድጉአቸው እንጂ አታስቆጡአቸው፣ ኤፌ. ፮፡፬።

እውነቱን ስለነገርኳችሁ ተቆጥታችሁኛል፣ ሞዛያ ፲፫፡፴። ይህንን ህዝብ በቁጣ እጎበኝዋለሁ፣ አልማ ፰፡፳፱።

በሁሉም ነገሮች ውስጥ የእርሱ እጅ እንዳለበት ከማይመሰክሩ በቀር፣ በምንም ሰው እግዚአብሔርን አያስቀይመውም፣ ት. እና ቃ. ፶፱፡፳፭። እኔ ጌታም በጎጥያተኞቹ ተናድጄአለሁ፣ ት. እና ቃ. ፳፫፡፴፪።

ቂሮስ

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የኢሳይያስን ትንቢት አይሁዶችን ቤተመቅደስ ለመገንባት ወደ ኢየሩ ሳሌም እንዲመለሱ፣ በዚህም በባቢሎን ምክሮነ ትን በክፍልም እንዲፈጸም ያደረገ የፋርሳዊው ንጉስ (፪ ዜና ፴፮፡፳፪–፳፫፣ ኢሳ. ፵፭፡፳፣ ፵፭፡፩)። ኢሳይያስ ትንቢት ያደረገው ከንጉሱ ስራ ፲፰ አመት በፊት ነበር።

ቂሽቁመን። *ደግሞም የጋድያንቶን ዘራፊዎች ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ በኋላ የጋድያንቶን ዘራፊዎች ተብለው የሚታወቁ ክፉ ሰዎች ቡድን መሪ (ሔለ. ፭፡፱–፲፪፣ ፪)።

ቃል። ኢየሱስ ክርስቶስ—*የክርስቶስ ቅድመ ምድራዊ ህይወት ተመልከቱ*

ቃል ኪዳን። *ደግሞም መሀላ፣ አዲስ እና የዘለአለም ቃል ኪዳን፣ የአብርሐም ቃል ኪዳን፣ የክህነት መሀላ እና ቃል ኪዳን ተመልከቱ*

በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለ ስምምነት፣

ነገር ግን በስምምነቱ እንደ እኩል አይደሉም። እግዚአብሔር የቃል ኪዳኑን ቅድመ ሁኔታን ይሰጣል፣ እናም ሰዎች እርሱ እንዲያደርጉ የሚጠይቃቸውን ለማድረግ ይስማማሉ። ከእዚያም እግዚአብሔር ሰዎችን አንዳንድ በረከቶች ለታዛዥነታቸው ቃል ይገባላቸዋል።

ሰረታዊ መርሆች እና ስነስርዓቶች የሚቀበሉት በቃል ኪዳን ነው። እንደዚህ አይነት ቃል ኪዳኖች የሚሰሩ የቤተክርስቲያን አባላት እነዚህን ለማክበር ቃል ይገባሉ። ለምሳሌ፣ አባላት በጥምቀት ከጌታ ጋር ቃል ኪዳን ይገባሉ እናም ቅዱስ ቁርባንን በመ ውሰድ ያን ቃል ኪዳን ያሳድሳሉ። ተጨማሪም ቃል ኪዳኖች በቤተመቅደስ ውስጥ ይሰራሉ። የጌታ ህዝ ቦች የቃል ኪዳን ህዝብ ናቸው እናም ከጌታ ጋር የገቡትን ቃል ኪዳኖች በሚያከብሩበት ጊዜ በይ በልጥ ይባረካሉ።

ቃል ኪዳኔንም ከአንተ ጋር አቆማለሁ፣ **ዘፍጥ. ፮፡፲፰**። ኪዳኔንም ብትጠብቁ፡ የተመረጠ ርስት ትሆኑልኛላችሁ፣ **ዘፀአ. ፲፱፡፭**። ከእነርሱና ከአ ማልክቶቻቸው ጋር ቃል ኪዳን አታድርግ፣ **ዘፀአ. ፳፫፡፴፪**። ለዘላለም ቃል ኪዳን በሰንበት ያርፉ ዘንድ ሰንበትን ይጠብቁ፣ **ዘፀአ. ፴፩፡፲፮**። ከእና ንተ ጋር ያደረግሁትን ቃል ኪዳን ለዘላለም አላ ፈርስም፣ **መሳ. ፪፡፩**። ከእርሱ ጋር ለመሥዋዕት ኪዳን የቆሙትን ቅዱሳኑን ሰብስቡለት፣ **መዝ. ፶፡፭** (ት. እና ቃ. ፶፯፡፳)።

ቅዱሱን ኪዳን አሰበ፣ **ሉቃ. ፩፡፸፪** (ት. እና ቃ. ፶፡፳፩)።

የእግዚአብሔር ሀይል በጌታ ቃል ኪዳን ህዝ ቦች ላይ ወረደ፣ **፩ ኔፊ ፲፬፡፲፡**። ለአብርሐም የተ ገባው ቃል ኪዳን በኋለኛው ቀናት ይሟላል፣ **፩ ኔፊ ፲፭፡፲፣፲**（ፒ ኔፊ ፲፯፡፭፣ ፲፩–፲፪፣ ፳፩፡፯፣ ሞር. ፱፡፴፯）። የቢንያም ህዝቦች ከእግዚአብሔር ጋር ፍላጎቱን ለማድረግ ቃል ኪዳን ለመግባት ፈቃ ደኞች ነበሩ፣ **ሞዛያ ፭፡፭**። ጥምቀት ሰው እግ ዚአብሔርን ለማገልገል ከእርሱ ጋር ለሚገባው ቃል ኪዳን ምስክር ነው፣ **ሞዛያ ፲፰፡፲፣፲**። የቃል ኪዳን ልጆች ናችሁ፣ **ፒ ኔፊ ፳፡፳፭–፳፮**። መላ እክት አብም ለሰው ልጆች የገባውን የቃል ኪዳን ስራ ያከናውናሉ እና ይፈፅማሉ፣ **ሞሮኒ ፯፡፳፱–፴፩**። የክርስቶስን ደም ማፍሰስ ቃል ኪዳን ነው፣ **ሞሮኒ ፲፡፴፣**።

በዚህች ቤተክርስቲያን አባል የሆነ እያንዳንዱ ሰው ሁሉንም ቃል ኪዳኖች ይጠብቁ፣ ት. እና ቃ. ፴፪፡፳፯። ቃል ኪዳንን የሚጠብቁ የተባረኩ ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፶፩፡፮። ይህን ቃል ኪዳን የሚሰብር ሹመቱን እና የቤተክርስቲያኗ ደረጃውን ያጣል፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፲፩–፲፪። ክህነትን የሚ ቀበሉ ሁሉ ይህን መሀላና ቃል ኪዳን ይቀበላሉ፣ ት. እና ቃ. ፶፬፡፴፱–፴። ቃል ኪዳናቸውን በመ ስዋዕት ለመከተል ፈቃደኛ ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፶፮፡፰። የጋብቻ ቃል ኪዳን ዘለአለማዊ ለመሆን ይችላል፣ ት. እና ቃ. ፭፴፪። ይህም ቃል ኪዳና ችን ይሆናል፣ በጌታ ስርዓቶች ሁሉ እንሄዳለን፣ ት. እና ቃ. ፭፴፮፡፱።

ቃየን

ደግምም አቤል፤ አዳም፤ የሚስጥር ስብሰባ፤ ግድያ ተመልከቱ

ታናሽ ወንድሙን አቤልን የገደለው የአዳም እና የሔዋን ወንድ ልጅ (ዘፍጥ. ፬፡፩–፲፮)።

መስዋዕቱ በጌታ ተቀባይነትን አላገኘም፣ **ዘፍጥ. ፬፡፫–፯** (ሙሴ ፭፡፭–፰፣ ፲፰–፳፮)። ወንድሙን አቤልን ገደለ፣ **ዘፍጥ. ፬፡፰–፲፬** (ሙሴ ፭፡፴፪–፴፮)። ጌታ ረገመው እናም ምልክት አደረገበት፣ **ዘፍጥ. ፬፡፲፭** (ሙሴ ፭፡፴፯–፴፱)።

አዳምና ሔዋን እርሱ ከመወለዱ በፊት ብዙ ወንድ እና ሴት ልጆች ወለዱ፣ **ሙሴ ፭፡፩–፫፣ ፲፮–፲፯**። ሰይጣንን ከእግዚአብሔር በላይ ወደደ፣ **ሙሴ ፭፡፲፫፣ ፲፰**። ከሰይጣን ጋር ቅዱስ ያልሆነ ቃል ኪዳን ገባ፣ **ሙሴ ፭፡፳፰–፴፩**።

ቄሳር

በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ የሮሜ ንጉስ ይታወቁ በት የነበረው ማዕረግ። በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ እንደ አለማዊ መንግስት ወይም ሀይል ምስል የሚ ጠቀሙበት ነው።

የቄሣርን ለቄሣር አስረክቡ፣ **ማቴ. ፳፪፡፲፰–፳፩** (ማር. ፲፪፡፲፯፣ ሉቃ. ፳፡፳፭፣ ት. እና ቃ. ፳፫፡፳፣ ፳፯)።

ቅናት

ደግምም መመኘት፤ ቅንዓት፣ መቅናት ተመልከቱ

በቅዱሣት መጻህፍት መሰረት፣ የሌላ ንብረት የሆነውን መፈለግ ትክክል አይደለም።

የአባቶችም አለቆች በዮሴፍ ቀንተው ወደ ግብፅ ሸጡት፣ **የሐዋ. ፯፡፱**። ፍቅር አይቀናም፣ **፩ ቆሮ. ፲፫፡፬**（ሞሮኒ ፯፡፴፭）። በትዕቢት ቅንዓት ይመ ጣል፣ **፩ ጢሞ. ፮፡፬**። ቅንዓትና አድመኛነት ባሉ በት ስፍራ በዚያ ሁከትና ክፉ ስራ ሁሉ አሉና፣ **ያዕ. ፫፡፲፮**።

ሰዎቹ እናም ጌታ እንዳይመቀኙ አዝዘአል፣ **፪ ኔፊ ፳፮፡፴**። በኔፊ ህዝቦች መካከል ቅናት አልነበረም፣ **፬ ኔፊ ፩፡፲፫–፲፰**።

የሰው ቅናት እና ቁጣዎች በህይወቴ ቀናት ሁሉ የየጊዜው እድሌ ነበርና፣ ት. እና ቃ. ፲፳፯፡፪።

ቅንነት

ደግምም ታማኝ፣ ታማኝነት፤ ጻድቅ፣ ጽድቅ ተመልከቱ

ፅድቅ፣ ታማኝነት፣ እና ልባዊነት።

እስከ ሞት ድረስ ፍጹምነቴን ከእኔ አላርቅም፣

ኢዮብ ፳፯፡፭። ጻድቅ ያለ ነውር ይሄዳል፣ ምሳ. ፳፡፯።

በሁሉም ጊዜ በተሰጣቸው በማንኛውም ነገር ታማኝ ሰዎች ነበሩ፣ አልማ ፱፮፡፳።

ጌታ ሀይረም ስሚዝ በልቡ ቅንነት ይወደዋል፣ አለ ጌታ፣ ት. እና ቃ. ፲፳፱፡፲፭።

ቅንዓት፣ መቅናት። *ደግሞም ቅናት ተመልከቱ*

በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ እንደተጻፉት፣ ቅንዓት ማለት፡ (፩) የጋለ መሆን እና ስለአንድ ሰው ወይም ነገር ጥልቅ ስሜት መኖር፣ እና (፪) በሰው መቅናት ወይም ሌላ በእናንተ ላይ እድል ይኖረዋል በማለት መጠራጠር።

የጋለ ስሜት መኖር፣ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝ፣ ዘፀአ. ፳፡፭ (ዘዳግ. ፭፡፱፣ ፮፡፲፭፣ ሞዛያ ፲፭፡፳፪)። ስለ ቅዱስ ስሜም እቀ ናለሁ፣ ሕዝ. ፴፱፡፳፭። በኢየሩሳሌምና በጽዮን ቀንቻለሁ፣ ዘካ. ፩፡፲፬።

መቅናት ወይም መጠራጠር፣ ቅንዓት ለሰው የቀላ ትኵሳት ነው፣ ምሳ. ፮፡ ፴፪–፴፭። አኪሽም በወንድ ልጁ መቅናት ጀመረ፣ ኤተር ፱፡፲።

ከቅናት እና ፍርሀት ራሳችሁን አስወግዱ፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፲።

ቅዱሳት መጻህፍት። *ደግሞም መፅሐፈ ሞርሞን፤ መፅሐፍ ቅዱስ፤ ቀኖና፤ ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች፤ የታላቅ ዋጋ ዕንቁ፤ የእግዚአብሔር ቃል ተመልከቱ*

የተቀደሱ የእግዚአብሔር ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ በተነሳሱ ጊዜ የተጻፉ እና የሚነገሩ ቃላት። ይፉ የሆኑ የቤተክርስቲያኗ የቀኖና ቅዱሳት መጻህፍት መፅሐፍ ቅዱስ፣ መፅሐፈ ሞርሞን፣ ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች፣ እና የታላቅ ዋጋ ዕንቁ ናቸው። ኢየ ሱስ እና የአዲስ ኪዳን ጸሀፊዎች የብሉይ ኪዳን መጻ ህፍትን እንደ ቅዱሣት መጻህፍት ይቆጥሯቸው ነበር (ማቴ. ፳፪፡፳፱፤ ዮሐ. ፭፡ ፴፱፤ ፪ ጢሞ. ፫፡ ፲፭፤ ፪ ጴጥ. ፩፡ ፳–፳፩)። ደግሞም የዘመን ቅድመ ተከ ተልን ተመልከቱ።

መጻሕፍትንም ሲከፍትልን ልባችን ይቃጠል ብን አልነበረምን፣ ሉቃ. ፳፬፡ ፴፪። እናንተ በመጻ ሕፍት የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ይመስላችኋ ልና እነርሱን ትመረምራላችሁ፤ እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው፣ ዮሐ. ፭፡ ፴፱።

የክርስቶስ ቃል ማድረግ ያለባችሁን ነገሮች በሙሉ ይነግራችኋል፣ ፪ ኔፊ ፴፪፡፫። ብዙዎች ወደ ቅዱሳን መፃሕፍትንም የሚያምኑ ፅኑ እናም የማይነቃነቁ ናቸው፣ ሔለ. ፲፭፡ ፯–፰።

ሰዎች በስህተት ቅዱስ መጻሃፍትን ያጣምማሉ እናም አይረዱዂቸውም፣ ት. እና ቃ. ፲፡ ፳፫። እነ ዚህ ቃላት የእኔ እንጂ የሰውም ሆነ የሰዎች አይደ ሉም፣ ት. እና ቃ. ፲፳፡ ፴፱–፴፯። የመፅሐፈ ሞር ሞን መምጣት ቅዱሣት መጻህፍት እውነት እንደ ሆኑ ማረጋገጫ ሰጠ፣ ት. እና ቃ. ፳፡ ፪፣ ፳–፲፪። ጊዜአቸሁን በቅዱስ መጽሐፍት ጥናትአከናውኑ፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡ ፭። ቅዱሳን መጽሐፍት ለቅዱሳን መማሪያነት ተሰጥተዋል፣ ት. እና ቃ. ፴፫፡ ፲፯። ቅዱሳን መጽሐፍት ለተመረጡት መዳን ይሆን ዘንድ ይሰጣል፣ ት. እና ቃ. ፴፭፡ ፳። በመፅሐፍ ቅዱስ እና በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ የሚገኙትን የወንጌሌን መርሆች ያስተምራሉ፣ ት. እና ቃ. ፴፪፡ ፲፪። እነዚሁን ነገሮች በተመለከተ በቅዱስ መጽሐፍቴ ውስጥ የተሰጡ ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፴፪፡ ፳፯–፴። በመንፈስ ቅዱስ ሲነሳሱ የሚናገሩት ማንኛውም ነገር ቅዱሣት መጻህፍት ይሆናል፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡ ፲፡ ፴።

የጠፉ ቅዱሣት መጻህፍት፣ በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ የተጠቀሱ ዛሬ የሌሉን ብሱ ቅዱስ ፅሁፎች ነበሩ፣ ከእነዚህ መፅሐፎች እና ጸሀፊዎች መካከል፡ የቃል ኪዳን መፅሐፍ (ዘፀአ. ፳፬፡ ፣)፣ የእግዚአብ ሔር የጦርነት መጽሐፍ (ዘኁል. ፳፩፡ ፲፬)፣ የያሻር መጽሐፍ (ኢያ. ፲፡ ፲፫፤ ፪ ሳሙ. ፩፡ ፲፰)፣ የሰሎሞን ታሪክ መጽሐፍ (፩ ነገሥ. ፲፩፡ ፴፩)፣ የሳሙኤል ታሪክ (፩ ዜና ፳፱፡ ፳፱)፣ ነቢዩ ናታን፡ (፪ ዜና ፱፡ ፳፱)፣ ነቢዩ ሸማያ (፪ ዜና ፲፪፡ ፲፭)፣ ነቢዩ በአዶ (፪ ዜና ፲፫፡ ፳፪)፣ ኢዩ (፪ ዜና ፳፡ ፴፴)፣ ባለ ራእዩ ታሪክ (፪ ዜና ፴፫፡ ፲፱)፣ ሄኖክ (ይሁዳ ፩፡ ፲፬)፣ እናም የዜናቅ፣ ኔፍም፣ እና ዜኖስ ቃላት (፩ ኔፊ ፲፱፡ ፣)፣ ዜኖስ (ያዕቆ. ፭፡ ፩)፣ ዜኖቅ እና ኤፅያስ (ሔለ. ፰፡ ፳)፣ የመታሰቢያ መፅሐፍ (ሙሴ ፮፡ ፭)፣ ወደ ቆሮንቶስ መልእክት (፩ ቆሮ. ፭፡ ፱)፣ ወደ ኤፌ ሶን መልእክት (ኤፌ. ፫፡ ፣)፣ ከሎዶቅያም መል እክት (ቁላ. ፬፡ ፲፮)፣ እና ከይሁዳ (ይሁዳ ፩፡ ፣)።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ ጻድቅ ሴት እና የአ ቤሜሌክ ሚስት (ሩት ፩–፬)። አቤሜሌክ እና ኑኃሚ ከረሀብ ለማምለጥ ቤተሰባቸውን ወደ ሞአብ ወሰዱ። አቤሜሌክ እና ሁለቱ ወንድ ልጆቿ ሞቱ፣ ኑኃሚ ወደ ቤተልሔም ከልጇ ሚስት ሩት ጋር ተመለሰች።

ኒቆዲሞስ። *ደግሞም ፈሪሳዊያን ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ ጻድቅ የአይሁዳ ገገር (ምናልባት የሳንሀድሪን አባል) እና ፈራሲዋ (ዮሐ. ፫፡፩)።

በምሽት ከኢየሱስ ጋር ተነጋገረ፣ ዮሐ. ፫፡፩–፳፩። ከፈራሲዋን ጋር ለኢየሱስ ተከራከረ፣ ዮሐ. ፯፡፣–፴፣። ለኢየሱስ መቃብር ሽቱ አመጣ፣ ዮሐ. ፲፱፡፴፱–፴፡

ና። *ኑ ተመልከቱ*

ናሆም

ትንቢቶቹን በ፯፻፴፪ እና በ፯፻፯ ም.ዓ. መካከል ትንቢቶቹን የመዘገበ የብሉይ ኪዳን የገሊላ ነቢይ።

ትንቢተ ናሆም፣ ምዕራፍ ፩ በዳግም ምፅዓት የም ድር መነደድ እና ስለጌታ ምህረት እና ሀይል ይና ገራል። ምዕራፍ ፪ በኋለኛው ቀናት ስለሚመጡት አስቀድሞ የሚነግረው ስለነነዌ መደምሰስ ይናገ ራል። ምዕራፍ ፫ ስለነነዌ አሰቃቂ መደምሰስ አስ ቀድሞ መንገርን ይቀጥላል።

ናቡከደነፆር። *ደግሞም ባቢሎን፣ ዳንኤል ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ ይሁዳን ያሸነፈ (፪ ነገሥ. ፳፬፡፩–፭) እና ኢየሩሳሌምን በጦር ሀይል የከበበ (፪ ነገሥ. ፳፭፡፣–፲፩) የባቢሎን ንጉስ። ነቢዩ ሌሂ በ፯፻ ም.ዓ. ንጉስ ናቡከደነፆር ንጉስ ሴዴቅያስ ንና ህዝቡን በሚወስድበት ጊዜ በምርኮ ወደ ባቢ ሎን መወሰድን ለማስወገድ ከኢየሩሳሌም እንዲ ሸሽ ታዘዘ፣ (፩ ኔፊ ፩፡፭–፲፣) (፪ ነገሥ. ፳፭፡፩፣ ፳–፲፯፣ ፳–፳፪) ዳንኤል ናቡከደነፆር ህልምን ተረ ጎመ (ዳን. ፪፣ ፭)።

ናታን። *ደግሞም ዳዊት ተመልከቱ*

በንጉስ ዳዊት ዘመን የነበረ የብሉይ ኪዳን ነቢይ። ለጌታ ቤተመቅደስ ለመገንባት ዳዊት ሀሳብ ሲያቅ ርብ፣ ጌታ ናታን ዳዊትን እንዳይገነባ እንዲነግረው አዘዘ። ናታን ዳዊት ከእርሱ ጆግናዎች አንዱ የሆ ነው የኦሪዮ ሞት ምክንያት ስለሆነ እናም የኦርዮን ሚስት ቤርሳቤህ ስላገባ ገሰጸው (፪ ሳሙ. ፲፪፡፩–፲፭፣ ት. እና ቃ. ፲፯፴፪፡፴፯–፴፱)። ሳዶቅ፣ ከና ታን ጋር፣ የዳዊትን ልጅ ሰለሞንን እንደ ንጉስ ቀቡ (፩ ነገሥ. ፩፡፴፯–፴፱፣ ፵፭)።

ናትናኤል። *ደግሞም በርተሎሜዎስ ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ የክርስቶስ ደቀመዛሙርት እና የፊልጶስ ጓደኛ (ዮሐ. ፩፡፵፭–፶፩)። በገሊላና ውስጥ ከቃና መጣ (ዮሐ. ፳፩፡፪)። ክርስቶስ ናትና ኤል ተንኮል የሌለው እስራኤላውያን ነው አለ (ዮሐ. ፩፡፵፯)። እርሱና በርተሎሜዎስ በአጠቃላይ አንድ ሰው ናቸው ተብሎ ይታሰባል (ማቴ. ፲፡፫፣ ማር. ፫፡፲፰፣ ሉቃ. ፮፡፲፬፣ ዮሐ. ፩፡፵፫–፵፭)።

ናዕማን። *ደግሞም አልሳዕ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የሶርያ ንጉስ ሰራዊት ወታደር። ደግሞም ለምጻም ነበር። በእስራኤላዊ ገደር ታማኝነት ምክንያት ወደ እስራኤል ነቢይ

ኤልሳዕን ለማየት ሄደ። እራሱን ትሁት በማድረግ እና ነቢዩ ኤልሳዕ እንደነገረው በዮርዳኖስ ወንዝ ውስጥ እራሱን ለሰባት ጊዜ በማጠብ ከለምጻምነቱ ዳነ (፪ ነገሥ. ፭፡፩–፲፬፤ ሉቃ. ፬፡፳፯)።

ናዝሬት። *ደግሞም ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልከቱ*

በገሊላ ባህር በስተምዕራብ በኮረብታዎች መካከል የምትገኝ መንድር። ናዝሬት የክርስቶስ የመጀመሪያ መኖሪያ ቦታ ነበር (ማቴ. ፪፡፳፫)። ኢየሱስ በናዝሬት በምኩራብ ውስጥ አስተማረ፣ እናም በኢሳይያስ ፡፡፩፡፩–፪ ውስጥ ያለውን ትንቢት እንዳሟላ አወጀ (ማቴ. ፲፫፡፶፭–፶፰፤ ማር. ፮፡፩–፮፤ ሉቃ. ፬፡፲፮–፴)።

ናሹ፣ ኢለኖይ (ዮ.ኤስ.ኤ.)

በ፲፡፲፱፴፱ (እ.አ.አ.) በኢለኖይ ግዛት ውስጥ በጓለኛው ቀን ቅዱሳን የተመሰረተ ከተማ። የሚገኘው ከሴንት ሉውስ ከተማ ፪፲ ማይል (፫፲፯ ኪሎ ሜትር) ከወንዙ በላይ በምስስፒ ወንዝ አጠገብ ነው።

በምዙሪ ግዛት በተሰደዱበት ምክንያት፣ ቅዱሳን ወደ ፪፲ ማይል (፫፲፯ ኪሎ ሜትር) ወደ ሰሜን ምስራቅ አካባቢ፣ የምስስፒ ወንዝን በመሻገር፣ ጥሩ ሁኔታዎችን ወደሚያገኙበት ወደ ኢለኖይ ሄዱ። ከጊዜ በኋላም፣ ቅዱሳን ገና ባልለመለመ ኮሜርስ ከተማ አጠገብ ምድር ገዙ። ከአንዳንድ ህንጻዎች በስተቀር፣ ይህ ምድር አረንቋማ ነበር ቅዱሳን ከም ድሩ ውሀውን አደረቁ እና ቤቶቻቸውን መሰረቱ። ጆሴፍ ስሚዝ ቤተሰቡን በእንጨት በተሰራ ትንሽ ቤት ውስጥ አስገባ። ኮሜርስ የሚባለው የከተማው ስም ወደ ናሹ ተቀየረ፣ ይህም ከዕብራውያን “ወብ ታማ” ከሚባለው ቃል ነው።

የትምህርት እና ቃል ኪዳኖች ብዙ ክፍሎች የተመዘገቡት በናሹ ውስጥ ነው (ት. እና ቃ. ፲፰፡–፲፰፱፤ ፲፡፴፱፤ ፲፡፴፭)። ቅዱሳን በናሹ ቤተመቅደስ እንዲገነቡ ተነገራቸው (ት. እና ቃ. ፲፰፡፡–፲፰፮–፲፰፯)። ከቤቶቻቸው በ፲፡፲፱፴፯ (እ.አ.አ.) ተነድተው ከመሰደዳቸው በፊት ቤተመቅደስን ሰሩ እናም የፅዮን ካስማዎችን አደራጁ። በመሳደዳቸው ምክንያት፣ ቅዱሳን ከእዚያ ቦታ ወጡና ወደ ምዕራብ ተጓዙ።

ኔሆር። *ደግሞም የካህን ተንኮል፣ የክርስቶስ ተቃዋሚ ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ የነበረ ክፉ ሰው። ኔሆር በኔፋውያን መካከል የካህናት ተንኮል ከሰሩት የመጀመሪያው ነበር። የህሰት ትምህርትን ካስተማረና ጌዴዎንን ከገደለ በኋላ፣ ኔሆር ለወንጀሉ በሞት ተቀጣ (አልማ ፤)። የኔሆር ተከታዮች ኔሆር ከሞተ ከረጅም ጊዜ በኋላ የክፉ ስራውንና ትምህርቱን ቀጠሉ።

አልማና አሙሌቅ በኔሆር ተከታይ ዳኛ ወደ እስር ቤት ተሰድደው ነበር፣ **አልማ** ፲፡፡–፲፡–፲፡፡። የተገ ደሉት የኔሆርን ኃይማኖት ተከታዮች ነበሩ፣ **አልማ** ፲፮፡፲፩። ብዙ የኔሆርን ስርዓት የሚከተሉ ነበሩ፣ **አልማ** ፷፩፡፡። ብዙዎቹን ወንድሞቻቸውን የገ ደሉት የኔሆር ስርዓት የሚከተሉ ነበሩ፣ **አልማ** ፷፡፡፡፷፡፡።

ኔፊ፣ የሔለማን ልጅ። *ደግሞም ሔለማን፣ የሔለማን ልጅ፣ ሌሂ፣ የኔፋውያን ሚስዮን ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ ታላቅ ኔፋውያን ነቢይና ሚስዮን።

የሔለማን ታላቅ ልጅ ነበር፣ **ሔለ.** ፫፡፷፩። ዋና ዳኛ እንዲሆን ተመደበ፣ **ሔለ.** ፫፡፴፯። እርሱና ወንድሙ ሌሂ ብዙ ላማናውያንን ወደ ወንጌል አመጣቸው፣ **ሔለ.** ፭፡፣፲–፣፲፱። በእሳት ተከበበ እናም ከእስር ቤት ተለቀቀ፣ **ሔለ.** ፭፡፷–፶፪። በአትክልት ስፍራ ግንብ ላይ ጸለየ፣ **ሔለ.** ፯፡፯–፣፡። የዋና ዳኛውን መገደል ገለጸ፣ **ሔለ.** ፡፡፡፡–፡፡፡፣ ፲፡፩–፴፡፡። በጌታ ሀይል ተሰጠው፣ **ሔለ.** ፣፡፫–፣፩። ጌታ ረሃብን እንዲያመጣ እና ረሀብ እንዲቆም ጠየቀ፣ **ሔለ.** ፣፩፡፫–፣፡፡።

ኔፊ፣ የሌሂ ልጅ። *ደግሞም ሌሂ፣ የኔፊ አባት፣ ኔፋውያን ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ የሌሂና የሳርያ ጻድቅ ልጅ ነው (፩ ኔፊ ፩፡፩–፴፣ ፪፡፲)። ኔፊ በእግዚአብሔር ቃል ታላቅ እምነት ነበረው (፩ ኔፊ ፫፡፣) እና ታላቅ ነቢይ፣ መዝገብ ጠባቂ፣ እና የህዝቡ መሪ ሆነ።

ታዛዥ ነበር እናም በእምነት ጸለየ፣ ፩ ኔፊ ፪፡፣፲፩። የህሰስ ሰሌዳዎችን ለማምጣት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ፣ ፩ ኔፊ ፫–፴። የእስማኤል ቤተሰብን ወደ ምድረበዳ ለማምጣት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ፣ ፩ ኔፊ ፣፡። ሌሂ የተቀበለውን አንድ አይነት ራዕይ ተቀበለ፣ ፩ ኔፊ ፣፡፣፲–፣፪፪፣ ፣፩። በራዕይ በህዝቡ ላይ ወደፊት የሚደርሰውንና የወንጌል ዳግም መመለስን ተመለከተ፣ ፩ ኔፊ ፣፪–፣፣፣። በህይወት ዛፍ ራዕይን ተረጎመ፣ ፩ ኔፊ ፣፣፡፡–፡፡፩–፴፣፩። ቀሰቱን ሰበረ ነገር ግን በእምነት ምግብን ለማግኘት ቻለ፣ ፩ ኔፊ ፣፣፩፡፣፣፡–፴፪። መርከብን ሰራ እና ወደ ቃል ኪዳን ምድር ተጓዘ፣ ፩ ኔፊ ፣፣፩–፣፣፡። ኔፋውያን እና ላማናውያን ተለያዩ፣ ፪ ኔፊ ፡፡። የመጨረሻ ምስክሩን ሰጠ፣ ፪ ኔፊ ፴፣፡።

፩ ኔፊ መፅሐፍ፣ ምዕራፍ ፩ እስከ ፣፡፡፡፡ በም ድረበዳ በህር ውስጥ ወደ ባህር እስከሚደርሱ ድረስ ተጓዙ። ፩ ኔፊ ፣፡፡፡፡–፡፡፣ በጌታ እንደተመሩት፣ ምንም እንኳን ላማን እና ላሙኤል ቢያምጹም ወደ ቃል ኪዳን ምድር ስለተጓዙበት ጉዞ ይናገራሉ። ምዕራፍ ፣፣፩–፡፡፪ ኔፊ መዝገቦችን ስለጠበቀበት አላማ ይናገራሉ (፩ ኔፊ ፪፣ ፣፣፩፡፣፣፡)፣ ይህም ሁሉም ጌታ

ቤዛቸውን እንዲያስታውሱ ለማሳመን ነው። ኢሳይ ያስን ጠቀሰ (፩ ኔፊ ፳–፳፩) እናም በተስፋ ሁሉም ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኛቸውና ቤዛቸው ለማ የት እንደሚችሉ የሚገልጸውን የኢሳይያስን ምል እክት ተረጎመ (፩ ኔፊ ፳፪፡፲፪)።

፪ የኔፊ መፅሐፍ፣ ምዕራፍ ፩–፱ ለልጆቹና ለት ውልዶቻቸው ከተሰጣቸው በረከቶች በተጨማሪ፣ ከመሞቱ በፊት የሰጣቸውን የሌሂን የመጨረሻ ትም ህርቶች እና ትንቢቶች የያዙ ናቸው። ምዕራፍ ፭ ኔፋያን ከላማናውያን ጋር የተለያዩበትን ምክንያት ይገልጻል። ኔፋውያን ቤተመቅደስ ሰሩ፣ የሙሴ ህግን አስተማሩ፣ እናም መዝገቦችን ጠበቁ። ምዕ ራፍ ፮–፲ የኔፊ ታናሽ ወንድም የያዕቆብ ቃላትን የያዙ ናቸው። ያዕቆብ የይሁዳን ታሪክ ገመገመ እና ስለመሲህ ተነበየ፣ አንዳንዶቹም ከነቢዩ ኢሳይያስ ፅሁፎች የተወሰዱ ነበሩ። በምዕራፍ ፲፩–፴፫ ውስጥ ኔፊ ስለክርስቶስ ስለነበረው ምስክር፣ ስለያዕቆብ ምስክር፣ ስለኋለኛው ቀናት ትንቢቶች፣ እና ከብ ሉይ ኪዳን መፅሐፈ ኢሳይያስ ውስጥ አንዳንድ ምዕ ራፎችን ይመዘግባል።

የኔፊ ሰሌዳዎች፣ ሰሌዳዎች ተመልከቱ

ኔፊ፣ የኔፊ ልጅ፣ የሔለማን ልጅ። *ደግሞም ኔፊ፣ የሔለማን ልጅ፤ ደቀ መዛሙርት ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ ከሞት በተነሳው ኢየ ሱስ ክርስቶስ ከተመረጡት አስራ ሁለት ደቀመዛ ሙርቶች መካከል አንዱ (፫ ኔፊ ፩፡፪–፫፤ ፲፱፡፱)። ይህ ነቢይ ለህዝቡ ጥቅም በሀይል ወደ ጌታ ጸለየ። ኔፊ የጌታን ድምፅ ሰማ (፫ ኔፊ ፩፡፲፩–፲፭)። ደግ ሞም ኔፊ በመላእክት ተነበገ፣ ዲያብሎሶችን አስ ወጣ፣ ወንድሙን ከሞት አስነሳ፣ እናም ለመካድ የማይቻል ምስክር ሰጠ (፫ ኔፊ ፯፡፲፭–፲፱፤ ፲፱፡፱)። ኔፊ የቅዱሣት መጻህፍት መዝገቦችን ጠበቀ (፫ ኔፊ ፩፡፪–፫)።

፫ የኔፊ መፅሐፍ፣ በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ የኔፊ ልጅ በሆነው ኔፊ የተጻፈ መፅሐፍ። ምዕራፍ ፩–፲ ስለጌታ መምጣት የተተነበዩትን መሟላት ያሳያሉ። የክርስቶስ መወለድ ምልክት ተሰጡ፤ ህዝቡ ንስሀ ገቡ፤ ነገር ግን ወደ ክፋታቸው ተመለሱ። በመጨ ረሻም አውሎ ንፋስ፤ የምድር መንቀጥቀጥ፣ ሀይ ለኛ ማዕበል፣ እና ታላቅ ድምሳሴ የክርስቶስን ሞት በምልክት ሰጡ። ምዕራፍ ፲፩–፳፰ ክርስቶስ ወደ አሜሪካ የመጣበትን ይመዘግባሉ። ይህም የ፫ ኔፊ መፅሐፍ ዋና ክፍል ነው። ብዙዎቹ የክርስቶስ ቃላት በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሰጣቸው ስብከቶች ጋር የሚመሳሰሉ ናቸው (ለምሳሌ፣ ማቴ. ፭–፯ እና ፫ ኔፊ ፲፪–፲፫)። ምዕራፍ ፳፱–፴ ለኋለኛው ቀን ሀገሮች ሞርሞን የተናገራቸውቃላትናቸው።

፬ የኔፊ መፅሐፍ፣ ይህ መፅሐፍ አርባ ዘጠኝ ቁጥ ሮች ብቻ ነው ያሉት፣ ነገር ግን የኔፋውያን ሶስት መቶ አመት ታሪክን የሚሸፍን ነው። በዚህ መዝ ገብ የጻፉ ከኔፊ በተጨማሪ ብዙ የጸሀፊ ትውልዶች ነበሩ። ቁጥሮች ፩–፲፱ በትንሳኤ ከተነሳው ጌታ ጉብ ኝት በኋላ፣ ኔፋውያንና ላማናውያን በሙሉ ወደ ወንጌሉ ተቀየሩ። ሰላም፣ ፍቅር፣ እና ስምምነት ነገሰ። ክርስቶስ እስከ ዳግም ምፅዓቱ ድረስ በም ድር እንዲቀሩ የፈቀደላቸው ሶስቱ ኔፋውያን ደቀ መዛሙርቱ (፫ ኔፊ ፳፯፡፱–፳) ህዝብን አገለገሉ። ኔፊ መዝገቡን ለልጁ አሞጽ አሳልፎ ሰጠ። ቁጥሮች ፲፱–፴፯ የአሞጽን (፳፡፱ አመታት) እና የልጁ የአ ሞጽን (፴፲፪ አመታት) አገልግሎትን መዝግበዋል። በ፴፪ ዓ.ም. ውስጥ፣ ትዕቢት እራሳቸውን በመደብ መከፋፈል እና ገንዘብ ለማግኘት የሀሰት ቤተክር ስቲያኖችን በጀመሩት ህዝብ መካከል ችግር መፍ ጠር ጀመረ (፱ ኔፊ ፩፡፳፱–፴፪)።

የ፴ ኔፊ የመጨረሻው ቁጥሮች ህዝቡ እንደገና ወደ ክፋት እንደተመለሱ ያሳያሉ (፱ ኔፊ ፩፡፴፩–፴፱)። በ፫፲፭ ም.ዓ. የአሞፅ ልጅ አሞፅ ሞተ እናም ወንድሙ አማሮን ለጥበቃ ቅዱስ መዝገቦችን ደበቀ። አማሮን በኋላም መዝገቡን የእራሱ የህይወት ጊዜ ብዙ ድርጊቶችን ለመዘገበውና ከእዚያም አሳጥሮ ለጻፋቸው ሞርሞን በእምነት አሳልፎ ሰጠ (ሞር. ፩፡፪–፬)።

ኔፋውያን። *ደግሞም ላማናውያን፤ መፅሐፈ ሞርሞን፤ ኔፊ፣ የሌሂ ልጅ ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ ያሉ፣ ብዙዎቹ የሌሂ ልጅ የነቢዩ ኔፊ ትውልዶች የሆኑ ህዝብ። ከላማና ውያን ጋር ተለያዩ እናም በአጠቃላይ ከላማናውያን በላይ ጻድቅ ነበሩ። ነገር ግን፣ በኋላም በኃጢያተኛ ነት ምክንያት በላማናውያን ተደመሰሱ።

ኔፋውያን ከላማናውያን ተለያዩ፣ ፪ ኔፊ ፭፡፭–፲፯። ላማናውያን ያልነበሩት ህዝቦች ኔፋውያን ነበሩ፣ ያዕቆ. ፩፡፲፫። ኔፋውያን ከሁሉም በሚበ ልጥ ምክንያት ተነሳስተው ነበር፣ **አልማ** ፴፫፡፲–፴፣ ፴፭። ኔፋውያን በሞሮኒ ዘመን አይነት ያለ ደስታ አልነበራቸውም፣ **አልማ** ፶፡፳፫። ኔፋውያን በጻድቅ ጻሎቶች ምክንያት ድነው ነበር፣ **አልማ** ፶፪፡፶፡ ኔፋውያን ባለማመን መነሙኑ፣ **ሔለ.** ፲፡፴፱–፴፭። ኢየሱስ በኔፋውያን መካከል አስተማረም አገለገ ለም፣ ፫ ኔፊ ፲፩፡፩–፳፯፡፲፪። ወደ ጌታ የተለወጡ ሁሉ፣ ሁሉም ነገሮች በጋራ ነበሩአቸው፣ ፬ ኔፊ ፩፡፪–፫። በህዝቡ ልብ ውስጥ ባለው የእግዚአብሔር ፍቅር የተነሳ በምድሪቱ ፀብ አልነበረም፣ ከሁሉም በላይ ደስተኛ የሆኑ ህዝብ ነበሩ፣ ፬ ኔፊ ፩፡፲፭–፲፯። ኔፋውያን መኩራትና ከንቱ መሆን ጀመሩ፣ ፬ ኔፊ ፩፡፴፫። በምድሪቱ ገፅ ሁሉ ደም መፋሰስ እናም እልቂት ሆነ፣ ሞር. ፪፡፲። ኔፋውያን በክፋት አደጉ እናም ሞርሞን እነርሱን ለመምራት እምቢ አለ፣

ሞር. ፫፡፱–፲፩። ከሀያ አራት በስተቀር፣ ኔፋውያን ሁሉ ተገደሉ፣ ሞር. ፮፡፮–፲፭። ክርስቶስን የማይክዱትን እያንዳንዱ ኔፋውያን ተገደሉ፣ ሞሮኒ ፩፡፪።

ኔፋውያን በኃጢያታቸው እና በእርኩስነታቸው የተነሳ ጠፉ፣ ት. እና ቃ. ፫፡፲፯። ኩራትን ተጠን ቀቁ፣ አለበለዚያም እንደ ኔፋውያን ትሆናላችሁ፣ ት. እና ቃ. ፴፯፡፴፱።

ኔፋውያን ደቀመዛሙርት። *ሶስቱ ኔፋውያን ደቀ መዛሙርቶች ተመልከቱ*

ንድፍ

ሰው አንዳንድ ውጤቶችን ለማግኘት የሚከተለው ሞዴል። በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ፣ ንድፍ በብዙ ጊዜ በአንዳንድ መንገድ ለመኖር ወይም አንድ ነገርን ለመገንባት ምሳሌ ማለት ነው።

ጌታ ለሙሴ በተሰጠው ንድፍ መሰረት እስራኤል ድንኳን እንዲገነቡ አዘዘ፣ **ዘፀአ.** ፳፭፡፰። ዳዊት ለሰለሞን የቤተመቅደስ ህንጻ ንድፍን ሰጠው፣ ፩ ዜና ፳፰፡፣ ፲፩–፲፫።

በእርሱ ያምኑ ዘንድ ላላቸው ሰዎች ምሳሌ እንድ ሆን ኢየሱስ ክርስቶስ አሳያቸው፣ ፩ ጢሞ. ፩፡፲፮።

እንዳትታለሉም ለሁሉም ነገሮች ንድፍ እሰጣ ችኋለሁ፣ ት. እና ቃ. ፶፪፡፲፬።

ንጹህ፣ ንጹህነት። *ደግምም ቅድስና፣ ንጹህ እና ርኩስ ተመልከቱ*

ከኃጢያት ወይም ጥፋት ነጻ መሆን፣ ታማኝ። ሰው ንጹህ የሚሆነው ሀሳቦቹ እና ስራዎቹ በሁሉም መንገድ የጸጹ ሲሆኑ ናቸው። ኃጢያት የሰራ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት፣ ንስሀ በመግባት፣ እና የወንጌልን ስነስርዓቶችን በመቀበል ንጹህ ለመሆን ይችላል።

እጆቹ የነጹ፡ ልቡም ንጹሕ የሆነ የጌታን በረከት ይቀበላል፣ መዝ. ፳፬፡፫–፭። እናንተ የእግዚአብሔር ዕቃ የምትሸከሙ ሆይ፣ ንጹሐን ሁኑ፣ ኢሳ. ፶፪፡፲፩ (ት. እና ቃ. ፲፯፫፡፩–፩)።

ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው፣ ማቴ. ፭፡፰ (፫ ኔፊ ፲፪፡፰)። ንጹሕ የሆነውን ነገር ሁሉ፡ እነ ዚህን አስቡ፣ ፊልጵ. ፬፡፰ (እ.አ. ፩፡፲፫)።

በልባችሁ ንፁህ የሆናችሁ ሁሉ፣ ራሳችሁን አቅኑ እናም አስደሳቹን የእግዚአብሔርን ቃል ተቀበሉ፣ ያዕቆ. ፫፡፪–፫። በዚያን ቀን በንፁህ ልባችሁና በን ፁህ እጆችሁ እግዚአብሔርን ለመመልከት ትችላላ ችሁን፣ አልማ ፭፡፲፱። በአምላክ ፊት ንፁህና እን ከን የለሽ ከሆኑ፣ ኃጢያትን ከመጥላት በቀር ሊመ ለከቱትም አልቻሉም፣ አልማ ፲፫፡፲፪። ክርስቶስ ንጹህ እንደሆነ ንጹህ ሁኑ፣ ሞሮኒ ፯፡፴፰ (ሞር. ፱፡፮)።

ክርስቶስ ንጹህ ህዝቦችን ለእራሱ ያቆያል፣ ት. እና ቃ. ፴፫፡፲፩። ጌታ ንጹህ የሆኑት እግዚአ ብሔርን የሚያዩበት ቤት በፅዮን እንዲገነባ አዘዘ፣ ት. እና ቃ. ፶፮፡፣ ፲–፲፯። ይህም ፅዮን ነውና—ልበ ንጹህ፣ ት. እና ቃ. ፶፮፡፳፩።

ንጹህ እና ርኩስ። *ደግምም ንጹህ፣ ንጹህነት፣ እድፍ፣ እድፍነት፣ የሙሴ ህግ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ ጌታ ለሙሴ እና ለጥንት እስራኤላውያን አንዳንድ ምግቦች ንጹህ፣ ወይም በሌላ አባባል፣ ለመብላት ብቁ እንደሆኑ ገለጸላ ቸው። እስራኤላውያን በንጹህ እና በርኩስ ምግ ቦች መካከል የሰጡት ልዩነት በህይማኖታቸውና በማህበራዊ ህይወታቸው ላይ ታላቅ ተፅዕኖ ነበ ራቸው። አንዳንድ እንስሳት፣ ወፎች፣ እና አሳ ለምግብ ንጹህ እና ተቀባይ ነበሩ፣ ሎሎችም ርኩስ እና የተከለከሉ ነበሩ (ዘሌዋ. ፲፩፣ ዘዳግ. ፲፬፡፫–፳)። አንዳንድ በሽተኛ ሰዎች እንደ ርኩስ ይቆ ጠሩ ነበር።

በመንፈሳዊ አመለካከት፣ ንጹህ መሆን ከኃጢ ያት እና ከኃጢያታዊ ፍላጎቶች ነጻ መሆን ነው። በዚህ አስተያየትም ያሉ ምግባረ ጥሩና ንጹህ ልብ ያለውን ሰው ይገልጻል (መዝ. ፳፬፡፬)። የእግዚአብ ሔር የቃል ኪዳን ህዝቦች ንጹህ ለመሆን ልዩ መመ ሪያ አላቸው (፫ ኔፊ ፳፡፴፩፣ ት. እና ቃ. ፴፳፡፴፪፣ ፲፴፫፡፭)።

እጆቹ የነጹ፡ ልቡም ንጹሕ የሆነ ወደ ጌታ ተራራ ይወጣል፣ መዝ. ፳፬፡፫–፭።

ማንንም ሰው ተራ ወይም ርኩስ ብላችሁ አት ጥሩ፣ የሐዋ. ፲፡፲፩–፳፳።

በንፁህ ልባችሁና በንፁህ እጃችሁ እግዚአብ ሔርን ለመመልከት ትችላላችሁ፣ አልማ ፭፡፲፱።

ጌታ ፅዩን ንጹህ እስክትሆን ድረስ ይገስጻታል፣ ት. እና ቃ. ፶፡፴፯። የጌታን ዕቃ የምትሸከሙ ንፁሃን ሁኑ፣ ት. እና ቃ. ፲፯፫፡፩–፭፣ ፲፩ (ኢሳ. ፶፪፡፲፩፣ ፲፩)።

ንጹህነት። *ደግምም ማመንዘር፣ ስሜታዊ፣ ስሜታዊነት፣ በጎነት፣ ዝሙት መፈጸም ተመልከቱ*

የወንዶች እና የሴቶች ወሲባዊ ንጹህነት።

ዮሴፍ የጲጥፋራ ሚስትን መገፋፋት ተቋቋመ፣ ዘፍጥ. ፴፱፡፣ ፯–፳፩ (ት. እና ቃ. ፵፪፡፳፩፡፣ ፶፱፡፯)። አታመንዝር፣ ዘፀአ. ፳፡፲፩። ልባም ሴት ለባልዋ ዘውድ ናት፣ ምሳ. ፲፪፡፬ (ምሳ. ፴፩፡፣)።

ሥጋችሁ . . . የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን፣ ፩ ቆሮ. ፮፡፲፯–፲፱። በንጽሕናም ለሚያምኑቱ ምሳሌ ሁን፣ ፩ ጢሞ. ፬፡፲፪።

ማንኛውም እርኩስ ነገር ከእግዚአብሔር ጋር ሊኖር አይቻለውም፣ ፩ ኔፊ ፲፡፳፩። እኔ ጌታ አም ላክ በሴቶች ንጹህነት እደሰታለሁ፣ ያዕቆ. ፪፡፳፯። ወሲባዊ ኃጢያት እርኩሰት ነው፣ አልማ ፴፱፡፩–

፲፫። ድንግልነት እና ምግባረ ጥሩነት ከሁሉም ነገሮች በላይ የተወደሰና ውድ ናቸው፣ ሞሮኒ ፱፡፱።
በንጹህነት እናምናለን፣ እ.አ. ፩፡፲፫።

ንፍታሌም። *ደግምም እስራኤል፣ ያዕቆብ፣ የይስሐቅ ልጅ ተመልከቱ*

ከያዕቆብ አስራ ሁለት ልጆች ስድስተኛው እና የራሄል ገረድ ባላ ሁለተኛ ልጅ ነበር (ዘፍጥ. ፴፡፣ ፯–፰)። ንፍታሌም አራት ወንድ ልጆች ነበሩት (፩ ዜና ፯፡፲፫)።

የንፍታሌም ጎሳዎች፣ ያዕቆብ ለንፍታሌም የሰጠው በረከቶች በአሪት ዘፍጥረት ፵፱፡፳፩ ውስጥ ተመዝግበዋል። ሙሴ ለጎሳው የሰጠው በረከት በአሪት ዘዳግም ፴፫፡፳፩ ውስጥ ተመዝግቧል።

ኖኅ፣ የመፅሐፍ ቅዱስ የአባቶች አለቃ። *ደግምም መርከብ፣ ቀስተ ዳመና፣ የኖኅ ዘመን የጥፋት ውሀ፣ ገብርኤል ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የላሜሕ ልጅ እና ከአዳም ጀምሮ አስረኛው የአባቶች አለቃ (ዘፍጥ. ፭፡፳፱–፴፪)። ስለክርስቶስ መሰከረ እናም ለኃጢያተኛ ትውልዶች ንስሀ መግባትን ሰበከ። ህዝቡ መልእክቱን ሲያስወግዱ፣ እግዚአብሔር ምድር ክፉዎችን ለማጥፋት በምትጥለቀለቅበት ጊዜ ቤተሰቡን እና የምድር ሁሉ እንስሳት እንዲኖሩበት መርከብ እንዲገነባ አዘዘው (ዘፍጥ. ፮፡፲፫–፳፪፣ ሙሴ ፰፡፲፯–፴)። ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ ኖኅ መላእኩ ገብርኤል እንደሆነ እና የደህንነትን ቁልፎች በመያዝ ከአዳም ተከታይ እንደሆነ አስተማረ።

እርሱ እና ልጆቹ ያፌት፣ ሴም፣ እና ሀም፣ እናም ባለቤቶቻቸው በእግዚአብሔር ትእዛዝ መሰረት መርከብን ሲገነቡ ድነው ነበር፣ ዘፍጥ. ፮–፰ (ዕብ. ፲፩፡፯፣ ፩ ጴጥ. ፫፡፳)። ጌታ ከሔኖክ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን ከኖህ ጋር አደሰ፣ ዘፍጥ. ፱፡፩–፲፯ (ጆ.ስ.ት.፣ ዘፍጥ. ፱፡፲፩፣ ፳፩–፳፩፣ ሙሴ ፯፡፴፱–፵፪)።

ኖኅ በአስር አመቱ ወደ ክህነት ስልጣን በማቱሳላ ተሾመ፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፵፪።

ሰዎች እርሱን ለመግደልም ፈለጉ፣ ነገር ግን የጌታ ሀይልም አዳነው፣ ሙሴ ፰፡፲፰። የጻድቅ ሰባኪ ሆነ እናም የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልን አስተማረ፣ ሙሴ ፰፡፲፱፣ ፳፫–፳፬ (፪ ጴጥ. ፪፡፭)።

ኖኅ፣ የዜኒፍ ልጅ

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ የነበረ ኃጢያተኛ ንጉስ። በኔፊ ምድር ውስጥ ኔፋውያንን መራ።

ኖኅ ብዙ ኃጢያቶችን ሰራ፣ ሞዛያ ፲፩፡፭–፲፭። ነቢዩ አቢናዲ እንዲገደል አዘዘ፣ ሞዛያ ፲፫፡፭ (ሞዛያ ፲፯፡፭፣ ፭–፰)። ኖኅ በእሳት ሞተ፣ ሞዛያ ፲፱፡፳።

አህዛቦች

በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ እንደሚጠቀሙበት፣ *አህዛብ* የተለያዩ ትርጉሞች አሉት። አንዳንድ ጊዜ ይህም የእስራኤል ዘር ያልሆኑ ህዝቦችን፣ አንዳንድ ጊዜ የአይሁዳ ዘር ያልሆኑ ህዝቦችን፣ እናም ምንም እንኳን በመካከላቸው የእስራኤል ደም ቢኖርም፣ አንዳንድ ጊዜ ወንጌሉ የሌላቸው ሀገሮች ንም ይጠቁማል። የኋለኛው የቃል ጥቅም በመፅሐፈ ሞርሞንና በትምህርት እና ቃል ኪዳኖች ውስጥ የሚጠቀሙበት ትርጉም ነው።

እስራኤላውያን እስራኤላውያን ያልሆኑትን አያገቡም (አህዛብ)፣ ዘዳግ. ፯፡፩–፫። ጌታ ለአሕዛብም ብርሃን ለመሆን ይመጣል፣ ኢሳ. ፵፪፡፮።

ጴጥሮስ ወንጌሉን ወደ አህዛብ እንዲወስድ ታዘዘ፣ የሐዋ. ፲፡፱–፴፭። እንኪያስ እግዚአብሔር ለአሕዛብ ደግሞ ንስሐን ሰጣቸው፣ የሐዋ. ፲፩፡፲፰። አይሁድ ብንሆን የግሪክ ሰዎችም ብንሆን በአንድ ቤተክርስቲያን ተጠምቀናልና፣ ፩ ቆሮ. ፲፪፡፲፫። በወንጌል አሕዛብ አብረው በክርስቶስ ወራሾች መሆን ይገባቸውል፣ ኤፌ. ፫፡፮።

መፅሐፈ ሞርሞን የተጻፈው በአህዛብ ነው፣ የመፅሐፈ ሞርሞን ርዕስ ገፅ (ሞር. ፫፡፲፯)። ከአህዛብ መካከል አንድ ሰው በብዙ ውኃዎች ላይ ሄደ፣ ፩ ኔፊ ፲፫፡፲፪። ሌሎች መፅሀፎች ከአህዛብ መጡ፣ ፩ ኔፊ ፲፫፡፴፱። የወንጌል ሙሉነት ወደ አህዛብ ይመጣል፣ ፩ ኔፊ ፲፭፡፲፫ (፫ ኔፊ ፲፮፡፮፣ ት. እና ቃ. ፳፡፱)። ይህ ምድር ለአህዛብ የነፃነት ምድር ይሆናል፣ ፪ ኔፊ ፲፡፲፩። አህዛብ ከወይራ ዛፍ ጋር ይመሳሰላል፣ ያዕቆ. ፭።

ወንጌሉ በአህዛብ ጊዜ ይመጣል፣ ት. እና ቃ. ፴፭፡፳፰ (ት. እና ቃ. ፲፱፡፳፯)። ቃል እስከ ምድር ዳርቻ፣ መጀመሪያ ወደ አህዛብ፣ እና ከዚያም ወደ አይሁድም ይዞራሉ፣ ት. እና ቃ. ፶፡፳–፲። ሰባዎቹ ለአህዛብ በሙሉ ልዩ ምስክሮች እንዲሆኑ ተጠርተዋል፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፳፭። መጀመሪያ ወደ አህዛብ እና ከዚያም ወደ አይሁዶች፣ ሁሉንም ሀገሮች እንዲጠሯቸው የቤተክርስቲያኔን ሽማግሌዎች ላኩ፣ ት. እና ቃ. ፲፴፫፡፳።

አለማመን። *ደግምም እምነት፣ ማመን ተመልከቱ*

በእግዚአብሔር እና በወንጌሉ እምነት ማጣት።

በአለማመናቸውም ምክንያት በዚያ ብዙ ተአምራት አላደረገም፣ ማቴ. ፲፫፡፶፰። በአለማመናቸውም ምክንያት በዚያ ብዙ ተአምራት አላደረገም፣ ማቴ. ፲፯፡፲፱–፳፩። አለማመኔን እርዳው፣ ማር. ፱፡፳፫–፳፬። ኢየሱስ ተነሥቶም ያዩትን ስላመኑአቸው አለማመናቸውንና የልባቸውን ጥንካሬ ነቀፈ፣ ማር. ፲፯፡፲፬። የማያምኑ ቢኖሩ አለ

ማመናቸው የእግዚአብሔርን ታማኝነት ያስቀራ ልን፣ ሮሜ ፫፡፫።

አንድ አገር እምነት በማጣት ከሚመነምንና ከሚ ሞት አንድ ሰው ቢሞት ይሻላል፣ ፮ ኔፊ ፱፡፲፫። የሚከዱበት ቀን ከመጣ፣ እንዲበተኑ እና እንዲጠፉ ያደርጋል፣ ፪ ኔፊ ፭፡፲–፲፩ (ት. እና ቃ. ፫፡፲፰)። ባለማመናቸው የእግዚአብሔርን ቃል ሊረዱት አል ቻሉም ነበር፣ ሞዛያ ፳፯፡፩–፭። ስለማያምኑ እን ደዚህ የሆነ ታላቅ ተአምራት ላሳያቸው አልቻል ኩም፣ ፫ ኔፊ ፲፱፡፴፭።

አዕምሮአችሁ ባለማመን ምክንያት ጨልሞባችሁ ነበር፣ ት. እና ቃ. ፴፬፡፴፩–፴፰።

አለማዊነት። *ደግሞም ሀብቶች፣ ከንቱ፣ ከንቱነት፣ ኩራት፣ ገንዘብ ተመልከቱ*

መንፈሳዊ ነገሮችን በመተው ለምድራዊ ሀብ ቶች እና ለንብረቶች ያለ ጻድቅ ያልሆነ ፍላጎት እና ጥረት።

ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጐ ድል ምን ይጠቅመዋል፣ ማቴ. ፲፮፡፳፮።

ልባቸውን በዓለም ከንቱ ነገሮች ላይ ያሳረፉ፣ አልማ ፬፡፰ (አልማ ፴፭፡፳፯)።

የዚህን አለም ነገሮች ወደጎን ትተዋያለሽ፣ ት. እና ቃ. ፳፭፡፲። ሰዎች ልባቸውን የአለም ነገ ሮች ላይ ያደርጋሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፳፭፡፴፭።

አለም። *ደግሞም ምድር፣ ስጋዊ፣ የሚሞት፣ ባቢሎን ተመልከቱ*

ምድር፣ ስጋዊ ሰው የሚፈተንበት ቦታ። በም ሳሌም፣ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የማያከብሩ ሰዎች።

ምድራዊ ህይወት፣ በዓለም ሳላችሁ መከራ አለ ባችሁ፣ ዮሐ. ፲፮፡፴፫።

እስከሞትም አትፍሩ፣ በዚህ አለም ደስታችሁ ሙሉ አይደለምና፣ ት. እና ቃ. ፲፩፡፴፯።

ትእዛዛትን የማያከብሩ ሰዎች፣ ዓለሙን ስለ ክፉ ታቸው እቀጣለሁ፣ ኢሳ. ፲፫፡፲፩ (፪ ኔፊ ፳፫፡፲፩)።

ዓለም ቢጠላችሁ ከእናንተ በፊት እኔን እንደ ጠላኝ እወቁ፣ ዮሐ. ፲፭፡፲፰–፲፱።

ትልቁና ሰፊው ህንፃ የዓለም ኩራት ነው፣ ፮ ኔፊ ፲፩፡፴፯።

አለም በሃጢያት እየበሰለ ነው፣ ት. እና ቃ. ፲፰፡፮። ከአለም ነገሮች ራስህን ንጹህ እና ነውር የሌለበት አድርግ፣ ት. እና ቃ. ፶፱፡፱። ታማኝ የሆነው እና የሚጸናውም አለምን ያሸንፋል፣ ት. እና ቃ. ፳፫፡፴፯። በአለም አይነት ኑሮ መኖር አይገባችሁም፣ ት. እና ቃ. ፶፭፡፲፫።

የአለም መጨረሻ፣ አዲስ አዲስ ምድር እፈጥራ ለሁ፣ የቀደሙትም አይታሰቡም፣ ኢሳ. ፳፭፡፲፯ (ራዕ. ፳፩፡፩፣ ኢ.አ. ፩፡፲)።

እንክርዳድ ተለቅሞ በእሳት እንደሚቃጠል፣ በዓለም መጨረሻ እንዲሁ ይሆናል፣ ማቴ. ፲፫፡፴፣ ፴፱ (ሚል. ፬፡፩፣ ያዕቆ. ፮፡፣ ፫)።

የወይኑን ስፍራዬን በእሳት እንዲቃጠል አደርገ ዋለሁ፣ ያዕቆ. ፭፡፫–፮ (ት. እና ቃ. ፰፬፡፰፫–፰፬)።

ጌታ ሰይጣንን እና ስራዎቹን በአለም መጨ ረሻ ያጠፋል፣ ት. እና ቃ. ፲፱፡፫። ምድር ብትሞ ትም፣ እንደገናም ህይወት ይሰጣታል፣ ት. እና ቃ. ፹፰፡፳፭–፳፮።

ጌታም ለሔኖክ እስከ አለም መጨረሻ ድረስ አሳ የው፣ ሙሴ ፯፡፳፯።

አለት። *ደግሞም ራዕይ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ወንጌል ተመልከቱ*

በምሳሌ፣ ጠንካራ መሰረት እና መደገፊያ የሆኑት ኢየሱስ ክርስቶስ እና ወንጌሉ (ት. እና ቃ. ፲፩፡፳፬፣ ፴፫፡፲፪–፲፫)። አለት ደግሞም እግዚአብሔር ወን ጌሉን ለሰው የሚያሳውቅበት ራዕይ መሆንም ይች ላል (ማቴ. ፲፮፡፲፭–፲፰)።

እርሱ አምላክ ነው፣ ሥራውም ፍጹም ነው፣ ዘዳግ. ፴፪፡፬። እግዚአብሔር ዓለቴ ነው፣ በእር ሱም እታመናለሁ፣ ፪ ሳሙ. ፳፪፡፪–፫። እጅም ሳይነካው ድንጋይ ከተራራው ተፈነቀለ፣ ዳን. ፪፡፴፬–፴፭።

በዓለት ላይም ተመሰርቷል፣ ማቴ. ፯፡፳፭ (፫ ኔፊ ፲፬፡፳፭)። ኢየሱስ ክርስቶስ የተናቀው ድን ጋይ ነው፣ የሐዋ. ፬፡፲–፲፩። ያም ዓለት ክርስቶስ ነበረ፣ ፩ ቆሮ. ፲፡፩–፬ (ዘፀአ. ፲፯፡፮)።

በአለት ላይ የሰራ እውነትን ይቀበላል፣ ፪ ኔፊ ፳፰፡፳፰። አይሁዶች የሚገነቡበት አለት [ክርስ ቶስን] አይቀበሉም፣ ያዕቆ. ፬፡፲፭–፲፯። በቤዛነት ዓለታችን ላይ ነው መሰረታችንን መገንባት ያለ ብን፣ ሔሊ. ፭፡፲፪። በክርስቶስ ትምህርት የሚገነባ በአለቱ ላይ ይገነባል እናም የጥፋት ውሀው ሲመጣ አይወድቅም፣ ፫ ኔፊ ፲፩፡፴፱–፴፣ (ማቴ. ፯፡፳፬–፳፯፣ ፫ ኔፊ ፲፳፡፲፪–፲፫)። ጠቢብ ሰው ቤቱን በአ ለት ላይ ሰራ፣ ፫ ኔፊ ፲፬፡፳፬።

በእኔ ዐለት ላይ ከተገነባችሁ ሊቋቋሟችሁ አይች ሉም፣ ት. እና ቃ. ፯፡፴፭። በዚህ አለት ላይ የተመ ሰረተም አይወድቅም፣ ት. እና ቃ. ፹፡፴፭።

እኔ የፅዮን ንጉስ፣ የሰማይ ዓለት፣ መሲሕ ነኝ፣ ሙሴ ፯፡፹፫።

አሉባልታ። *ደግሞም ክፉ መናገር፣ ወሬ ተመልከቱ*

ከእዚያ ሰው ፍቃድ ሳይኖር ስለ ሌላ ሰው የግለ ሰብ ተጨባጭ ነገሮችን ወይም መረጃዎችን መካ ፈል።

ሰዎች ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር ሁሉ መልስ ይሰጡበታል፣ ማቴ. ፲፪፡፴፮። ቅዱሳን የማይገባ

ውንም እየተናገሩ፣ ለፍላፊዎችና በነገር ጣልቃ ገቢ ዎች እንዳይሆኑ ተገስጸዋል፣ ፩ ጢሞ. ፭፡፣ ፲፩–፲፡፡

በባልጀራህ ላይ እርኩሰትን አትናገር፣ ት. እና ቃ. ፵፪፡፣ ፳፯፡፡ በንግግርህ በሙሉ ወንድ ሞችህን አጠናክር፣ ት. እና ቃ. ፲፰፡፣ ፲፡

አልማ፣ የአልማ ወንድ ልጅ። *ደግሞም ሽማግሌው አልማ፤ አሙሌቅ፤ የሞዛያ ልጆች ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ የኔፋውያን ህዝቦች የመጀመሪያ ዋና ዳኛ እና ነቢይ። በወጣትነቱ ቤተ ክርስትያኗን ለማጥፋት ፈለገ (ሞዛያ ፳፯፡፣ ፳–፲)። ነገር ግን፣ መላእክት ተገለጸለት እና ወደ ወንጌሉም ተቀየረ (ሞዛያ ፳፯፡፣ ፳–፳፱፤ አልማ ፴፯፡፣ ፯–፳፯)። በኋላም የዋና ዳኛ ሀላፊነቱን ህዝቦችን ለማስተማር ዘንድ ተወው (አልማ ፩፡፲፩–፳)።

መፅሐፈ አልማ፣ የነብያት አልማ፣ የአልማ ልጅ፣ እና የእርሱም ልጅ ሔለማን ፅሁፎች በእጥ ረት ተፅፎበት ያለ በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ የተ ለየ መፅሐፍ። በመፅሐፉ ውስጥ የሚገለጹት ድርጊ ቶች የደረሱት በግምት ከ ፣፲፩ እስከ ፵፪ ም.ዓ. ነበር። መፅሀፉ ፳፫ ምዕራፎች አሉት። ምዕራፍ ፩–፬ የኔሆር እና የአምሊካይ ተከታዮች በኔፋውያን ላይ ያመጹ በትን ይገልጻሉ። የዚህ ውጤት ጦርነት በኔፋው ያን ታሪክ ውስጥ ከነበሩት በላይ የሚያጠፋ ነበር። ምዕራፍ ፭–፲፯ የአልማን የመጀመሪያ የሚስዮን ጉዞዎች፣ በተጨማሪም የጥሩው እረኛ ስብከቱን (አልማ ፭) እና ከአሙሌቅ ጋር በአሞኒያሀ ውስጥ የሰበከውን ፅሁፍ ይዘዋል። ምዕራፍ ፲፯–፳፯ የሞዛያ ወንድ ልጆችን እና በላማናውያን መካከል ስላደረ ጉት አገልግሎት ፅሑፍ ይዘዋል። ምዕራፍ ፳፰–፴፪ የአልማ ከሁሉም በላይ አስፈላጊ የነበሩትን አንዳ ንድ ስብከቶች ይዘዋል። በምዕራፍ ፴፪ ውስጥ አልማ ቃልን ከዘር ጋር አነጻጸረ፣ በምዕራፍ ፴፯ ውስጥ ለልጁ ሔለማን የቅያሬ ታሪኩን ነገረው። ምዕራፍ ፴፱–፴፪ አልማ በስነምግባር መተላለፍ ተካፋይ ለነ በረው ለልጁ ቆሪያንተን የሰጠውን ምክር ይመዘግ ባሉ፣ ይህ አስፈላጊ ስብከት ፍትህን፣ ምህረትን፣ ትንሳኤን፣ እና የኃጢያት ክፍያን ይገልጻል። ምዕ ራፍ ፴፭–፴፫ የዛ ጊዜ የኔፋውያን ጦርነቶችን እና በሀጋዝ ዘመን ስደቶችን ይገልጻሉ። እንደ ሻምበል ሞሮኒ፣ ቴአንከም፣ እና ሊሀይ አይነት ታላቅ መሪ ዎች በብርቱ እና ጊዜአዊ ስራዎቻቸው ኔፋውያንን ለመጠበቅ ረዱ።

አልሳዕ

የሰሜን እስራኤል መንግስት የብሉይ ኪዳን ነቢይ እና የሀገሯ የተለያዩ ንጉሶች የታመነ አማካሪ።

ኤልሳዕ አለቃው ኤልያስ የታወቀበት የሚን በለበል ጉጉት ሳይኖረው፣ የረጋና አፍቃሪ ጸባይ የነበረው ነበር። የእርሱ የሚጠቀሱት ታምራቶቹ (፪ ነገሥ. ፪–፭፣ ፰) በኤልያስ ምትክ ነቢይ ሲሆን (፪ ነገሥ. ፪፡፣ ፱–፲፪) በእውነትም የኤልያስን ሀይል እንደተቀበለ የሚመሰክሩ ነበሩ። ለምሳሌ፣ የሚ መር ምንጭ ውሀን ፈወሰ፣ የዮርዳኖስ ወንዝ ውሀ ዎችን ከፋፈለ፣ የባልቴት ዘይትን አባዛ፣ ወንድ ልጅን ከሞት አስነሳ፣ ሰውን ከለምጽ ፈወሰ፣ የብ ረት ምሳር በውሀ ላይ እንዲንሳፈፍ አደረገ፣ እናም ሶሪያውያኖቹን አይነ ስውር አደረጋቸው (፪ ነገሥ. ፪–፮)። በኢዩራም፣ በኢዩ፣ በኢዮአካዝ፣ እና በኢዮአስም ንግስና ጊዜ ከሀምሳ አመት በላይ አገ ለገለ።

የኤልያስን መጐናጸፊያ ተቀበለ፣ ፪ ነገሥ. ፪፡፣ ፲፫። የባልቴት ዘይትን አባዛ፣ ፪ ነገሥ. ፬፡ ፩–፯። የሱነማይቱን ወንድ ልጅ ከሞት አስነሳ፣ ፪ ነገሥ. ፬፡ ፣፴–፴፯። ሶሪያውያኑን ናዕማንን ፈወሰ፣ ፪ ነገሥ. ፭፡ ፩–፲፬። የሶሪያውያን ወታደ ሮች አይነ ስውር አደረጋቸው፣ እና የአገልጋዩን አይኖች ከፈተ፣ ፪ ነገሥ. ፮፡ ፳–፳፫፡፡

አልዓዛር። *ደግሞም ማርታ፤ የቢታንያ ማርያምን ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ የማርታና የማርያም ወን ድም። ኢየሱስ ከሞት አስነሳው (ዮሐ. ፲፩፡ ፩–፴፬፣ ፲፪፡ ፩–፪፣ ፱–፲፩)። ይህም ኢየሱስ በምሳሌ ባስተ ማረው ውስጥ የነበረው ለማኙ አልዓዛር አይደለም (ሉቃ. ፲፮፡ ፲፱–፴፩)።

አልፋ እና ኦሜጋ። *ደግሞም ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልከቱ*

አልፋ የግሪክ ፊደል የመጀመሪያ ፊደል ነው፤ ኦሜጋ የመጨረሻው ነው። እነዚህ ለኢየሱስ ክር ስቶስ የተሰጡ ስሞች እና ክርስቶስ መጀመሪያ እና መጨረሻ እንደሆነ እንዲያሳዩ የሚጠቀሙባቸው ምልክቶች ናቸው (ራዕ. ፩፡ ፣፳፤ ት. እና ቃ. ፲፱፡ ፩)።

አመስጋኝ፣ ምስጋናን፣ ምስጋና መስጠት። *ደግሞም መባረክ፣ የተባረከ፣ በረከት፤ ማምለክ ተመልከቱ*

ከእግዚአብሔር ከተቀበልነው በረከቶች የምን ሰጠው ምስጋና። ምስጋናን መግለፅ እግዚአብሔ ርን ያስደስታል፣ እናም እውነተኛ ማምለክ ምስጋና በተጨማሪ አለው። ለጌታ ለሁሉም ነገሮች ምስጋና መስጠት ይገባናል።

እግዚአብሔርን ማመስገን መልካም ነው፣ መዝ. ፣፶፪፡ ፩። በምስጋና ወደ ፊቱ እንድረስ፣ መዝ. ፣፺፭፡ ፩–፪። አመስግኑት፡ ስሙንም ባርኩ፣ መዝ. ፻።

ማመስገንን አትተው፣ ኤፌ. ፭፡ ፲፭–፲፯። የም ታመሰግኑም ሁኑ፣ ቄላ. ፫፡ ፣፲፭። በረከትና ክብር ጥበብም ምስጋናም ውዳሴም ኃይልም ብርታትም

ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ለአምላካችን ይሁን፣ ራዕ. ፯፡፲፪።

በረከትና ክብር ምስጋናም ውዳሴም ለአምላካችን ይሁን፣ ሞዛያ ፪፡፲፱–፳፩። በየቀኑ በምስጋና ኑሩ፣ **አልማ** ፴፩፡፴፰። ጠዋት ከመኝታህ በምት ነቃበት ጊዜ ልብህ ሁሉ እግዚአብሔርን በማመስገን ይሞላ፣ **አልማ** ፴፯፡፴፯።

ሁሉንም ነገሮች በጸሎትና በምስጋና አድርጉ፣ ት. እና ቃ. ፴፯፡፯። ምስጋናዎችን ለእግዚአብሔር መስጠት አለባችሁ፣ ት. እና ቃ. ፴፯፡፴፪። ምስጋና በመስጠት እነዚህን ነገሮች አድርጉ፣ ት. እና ቃ. ፶፱፡፲፭–፳፩። ከጌታ እጅ ለሁሉም ነገሮች ምስጋና ባለው ልብ በረከትን ተቀበለ፣ ት. እና ቃ. ፳፪፡፯። ሁሉንም ነገሮች በምስጋና የሚቀበል ባለ ክብር ይሆናል፣ ት. እና ቃ. ፫፳፡፲፱። በሁሉም ነገሮች ምስጋናዎች ስጡ፣ ት. እና ቃ. ፶፳፡፩ (፩ ተሰ. ፭፡፲፳)። ጌታን በምስጋና ጸሎትና በምስጋና አምልኩ፣ ት. እና ቃ. ፲፴፯፡፳፯።

አመራር። ቀዳሚ አመራር *ተመልከቱ*

አመጽ። *ደግሞም ኃጢያት፤ ማጉረምረም፤ ክህደት፤ ዲያብሎስ ተመልከቱ*

በእርሱ የተመረጡትን መሪዎች ለመከተል እምቢ በማለት እና ትእዛዛቱን በፈቃደኝነት ባለ ማክበር የጌታን ትእዛዝ መጣስ ወይም እርሱን መቃወም።

በእግዚአብሔር ላይ አታምፁ፣ ዘኁል. ፲፬፡፱። ክፉ ሰው ዓመፃን ብቻ ይሻል፣ ምሳ. ፲፯፡፲፩። ለዓመፀኞች ልጆች ወዮላቸው፣ ኢሳ. ፴፡፩።

ጌታም በእርሱ ላይ ያመፀውንና በኃጢያት የሞተውን አያድንም፣ ሞዛያ ፲፭፡፳፯። አምሊኪውያን በእግዚአብሔር ላይ አመጹ፣ **አልማ** ፫፡፲፳–፲፱።

አመጸኞች በብዙ ሐዘን ይወጋሉ፣ ት. እና ቃ. ፩፡፫። የጌታ ቁጣ በአማጸኞቹ ላይ ነዷል፣ ት. እና ቃ. ፶፯፡፩ (ት. እና ቃ. ፳፫፡፩–፯)።

ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ ዐመፀ፣ **ሙሴ** ፬፡፫።

አሙሌቅ። *ደግሞም አልማ፣ የአልማ ወንድ ልጅ ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ የአልማ ልጅ አልማ ሚስዮን የጉዞ ጓደኛ።

በመላእክት ተጎብኝቶ ነበር፣ **አልማ** ፰፡፳፣ ፲፡፯። አልማን በቤቱ ተቀበለ፣ **አልማ** ፰፡፳፩–፳፯። ለአሞኒያሃ ህዝቦች በሀይል ሰበከ፣ **አልማ** ፰፡፳፱–፴፪፣ ፲፡፩–፲፩። የኔፊ፣ የሌሂ፣ እና የም ናሴ ተወላጅ ነበር፣ **አልማ** ፲፡፪–፫። ስለእውነት መሰከረ፣ **አልማ** ፲፡፬–፲፩። ህዝቦችን ንስሀ እን ዲገቡ ጠራቸው እና ተወገደ፣ **አልማ** ፲፡፲፪–፴፪። ከዚዝሮም ጋር ተከራከረ፣ **አልማ** ፲፩፡፳–፳፮። ከሞት ስለመነሳት፣ ስለፍርድ፣ እና ዳግሞ መመለስ አስተማረ፣ **አልማ** ፲፩፡፳፯–፳፭። የሚያምኑትን ሰማእትነትን ለማቆም ፈለገ፣ **አልማ** ፲፬፡፱–፲። ከአልማ ጋር ታስሮ ነበር፣ **አልማ** ፲፬፡፲፬–፳፫። በወህኒ ቤቱ የታሰረበትን ሲባጎ በእምነት በጠሰ፣ **አልማ** ፲፬፡፳፩–፳፱። ስለኀጢያት ክፍያ፣ ስለም ህረት፣ እና ስለፍትህ መሰከረ፣ **አልማ** ፴፩፡፳–፲፯። ስለጸሎት አስተማረ፣ **አልማ** ፴፩፡፲፯–፳፳። ንስሀ መግባታቸውን እንዳያዘገዩ ሰዎችን አበረታታ፣ **አልማ** ፴፩፡፴–፴፭። የአልማ እና የአሙሌቅ እምነት የወህኒ ቤቱ ግድግዳ እንዲወድቅ አደረጉ፣ **ኤተር** ፲፪፡፲፫።

አማላጅ። *ደግሞም ኢየሱስ ክርስቶስ፤ የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ ተመልከቱ*

ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ጋር አማላጃችን ነው (ሞሮኒ ፯፡፳፳) እና ከእርሱም ጋር ምክንያታችንን ይለምንልናል፡ የሚማለድ ወይም መካከለኛ። ኢየሱስ ክርስቶስ በሰው እና በእግዚአብሔር መካከል የሚማለድ ነበር። የእርሱ የኃጢያት ክፍያ ሰዎች ለኃጢያታቸው ንስሀ ለመግባት እና ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅ የሚቻልበት መንገድ ሰራ።

በኢየሱስ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም፣ **ዮሐ.** ፲፬፡፮። በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፣ ፩ ጢሞ. ፪፡፭። ክርስቶስ በኪዳን ደግሞ መካከለኛ እንደሚሆን በዚያ ልክ እጅግ የሚሻል ነው፣ ዕብ. ፰፡፮ (ዕብ. ፱፡፲፭፣ ፲፪፡፳፬፣ ት. እና ቃ. ፻፲፡፲፱)። ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ዘንድ አማላጃችን ነው፣ ፩ **ዮሐ.** ፪፡፩ (ት. እና ቃ. ፻፲፡፱)።

ኢየሱስ ለሰው ልጆች ሁሉ ይማለዳል፣ ፪ ኔፊ ፪፡፱ (ዕብ. ፯፡፳፭)። ቅዱሱ መሲህ ለሰው ልጆች ሁሉ ያማልዳል፣ ፪ ኔፊ ፪፡፱ (ኢሳ. ፶፫፡፲፪፣ ሞዛያ ፲፭፡፲፪)። በታላቁ አማላጅ ተመኩ፣ ፪ ኔፊ ፪፡፳፯–፳፳። ኢየሱስ በሞት ላይ ድልን አገኘ፣ ለሰው ልጆች እንዲማልድ ኃይልን ሰጠው፣ ሞዛያ ፲፭፡፳።

ከአብ ዘንድ አማላጃችሁ ነኝ፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፭። ኢየሱስ ክርስቶስ ምክንያታችሁን ይማጸንላቸኋል፣ ት. እና ቃ. ፴፭፡፫–፭። የአዲስ ኪዳን አማላጅ በሆነው ኢየሱስ ፍጹም ሆነናል፣ ት. እና ቃ. ፫፯፡፳፱።

አማሌቃዊ (ብሉይ ኪዳን)

በፋራን በሀር ውስጥ በአራባ እና በሜድትሬኒያን መካከል የኖሩ የአረብ ግንድ። ከእብራውያን ጋር ከመሴ ጀምሮ (ዘፀአ. ፲፯፡፰) እስከ ሳኦል እና ዳዊት ዘምን (፩ ሳሙ. ፲፭፡፣ ፳፯፡፰፣ ፴፣ ፪ ሳሙ. ፰፡፲፩–፲፪) ድረስ ሁልግዜም በጦርነት ይዋጉ ነበር።

አማሌቅያውያን (መፅሐፈ ሞርሞን)

ላማናውያን ከኔፋውያን ጋር እንዲዋጉ የመሩ

ሀይማኖትን የከዱ ኔፋውያን (አልማ ፳፭–፳፱፤ ፴፫)።

አማኑኤል። *ደግምም ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልከቱ*

ከኢየሱስ ክርስቶስ ስሞች አንዱ። ይህም “እግዚአብሔር ከእኛ ጋር” የሚል ትርጉም ካለው የዕብራውያን ቃል የመጣ ነው።

አማኑኤል እንደ እግዚአብሔር ቤዛነት ምልክት የተሰጠ ስም-ርዕስ ነው (ኢሳ. ፯፡፲፬)። ኢሳይያስ የጠቀሰው አማኑኤል እንደ ኢየሱስ በስጋ መወለድ ትንቢት በማቴዎስ ተጠቁሟል (ማቴ. ፩፡፲፰–፳፫)። ስሙም በኋለኛው ቀን ቅዱሳት መጻህፍት ውስጥ ታይቷል (፪ ኔፊ ፲፯፡፲፬፣ ፲፰፡፰፣ ት. እና ቃ. ፲፳፰፡፳፪)።

አሜን። *ደግምም ጸሎት ተመልከቱ*

“ይህም ይሁን” ወይም “እንዲህም ነው” ማለት ነው። አሜን የሚባለው ልባዊ ወይም የተከበረ ተቀባይነት እና ስምምነትን (ዘዳግ. ፳፯፡፲፬–፳፮) ወይም እውነትነት (፩ ነገሥ. ፩፡ ፴፯) ለማሳየት ነው። ዛሬ በጸሎቶች፣ በምስክርነቶች፣ እና ንግግሮች መጨራሻ ላይ፣ ጸሎትን ወይም ምልዕክትን የሰሙት ተቀባይነት እና ስምምነትን ለማሳየት በደንብ የሚሰማ አሜን ይላሉ።

በብሉይ ኪዳን ጊዜዎች፣ ሰው መሃላ ሲገባ አሜን ማለት ነበረበት (፩ ዜና ፲፮፡፣ ፴፭–፴፮፣ ነህ. ፭፡፲፫–፲፫፣ ፰፡፪–፯)። ክርስቶስ “አሜን የሆ ነው፡ የታመነውና እውነተኛው ምስክር” ተብሎ ተጠርቷል (ራዕ. ፫፡፲፬)። በነቢያት ትምህርት ቤት አሜንም ደግሞ እንደ ቃል ኪዳን ምልክት አገልግሏል (ት. እና ቃ. ፹፰፡፪፣ ፪፴፫–፪፴፭)።

አምሊካያህ

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ በላማናውያን መካከል ሀይል ያገኙ እና በኔፋውያን ላይ የመሩአቸው የኔፋውያን ከዳተኞች (አልማ ፴፯–፴፩)።

አምሊካይ፣ አምሊካውያን

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ በዳኛዎች ዘመነ መንግስት ንጉስ ለመሆን ፍላጎት የነበራቸውን ኔፋውያንን ይመራ የነበረ ሰው። አምሊካውያን ተብለው የተጠሩት እነዚህ ኔፋውያን በእግዚአብሔር ላይ በግልፅ አመጹ፣ ለዚህም ተረግመው ነበር (አልማ ፪–፫)።

አምላክነት። *ሰው፣ ሰዎች—የሰው እንደ እግዚአብሔር አይነት ለመሆን ያለው ችሎታ፣ ከፍተኛነት፣ የዘለዓለም ህይወት ተመልከቱ*

አምልኮ። *ማምለክ ተመልከቱ*

አምስቱ መጻህፍት። *ደግምም ሙሴ፣ ብሉይ ኪዳን፣ ኦሪት ዘኁልቁ፣ ኦሪት ዘሌዋውያን፣ ኦሪት ዘዳግም፣ ኦሪት ዘፀአት፣ ኦሪት ዘፍጥረት ተመልከቱ*

ለብሉይ ኪዳን የመጀመሪያ አምስት መፅሐፎች፣ ኦሪት ዘፍጥረት፣ ኦሪት ዘፀአት፣ ኦሪት ዘሌዋውያን፣ ኦሪት ዘኁልቁ፣ ኦሪት ዘዳግም፣ የተሰጡ ስሞች። አይሁዶች እነዚህን መፅሐፎች ቶራ ወይም የእስራኤል ህግ ብለው ይጠሯቸዋል። በሙሴ ተፅፈው ነበር (፩ ኔፊ ፭፡፣–፣፩)።

አሞን፣ የሞዛያ ወንድ ልጅ። *ደግምም ሞዛያ፣ የቢንያም ልጅ፣ አንቲ-ኔፊ-ሌሂ፣ የሞዛያ ልጆች ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ የንጉስ ሞዛያ ወንድ ልጅ። አሞን ትጋታዊ ጥረቱ ብዙ መንፈሶችን ወደ ክርስቶስ ለመቀየር እንደረዳ ሚስዮን አገለገለ።

ቤተክርስትያኗን ለማጥፋት የፈለገ አረመኔ ነበር፣ **ሞዛያ** ፳፯፡፡–፣፣ ፴፱። ለእርሱ እና ለጓደኞቹ መላእክት ተገለጠላቸው፣ **ሞዛያ** ፳፯፡፣፩። ንስሀ ገባ እና የእግዚአብሔርን ቃል መስበክ ጀመረ፣ **ሞዛያ** ፳፯፡፴፪–፳፰፡፡። በንጉስነት ለመመደብ እንቢ አለ እና በምትኩ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስበክ ወደ ላማናውያን ምድር ሄደ፣ **አልማ** ፣፣፯፡፣–፣፩። ለመመሪያ ጾመ እና ጸለየ፣ **አልማ** ፣፣፯፡፡–፣፩። ታስሮ ወደ ንጉስ ላሞኒህ ተወሰዶ ነበር፣ **አልማ** ፣፣፯፡፳–፳፩። የላሞኒህን መንጋዎች አዳነ፣ **አልማ** ፣፣፯፡፳፩–፴፴። ለላሞኒህ ሰበከ፣ **አልማ** ፣፣፡፡፡–፣፣፩፡፣፣፫። እግዚአብሔርን አመሰገነ እና በደስታ ተሸነፈ፣ **አልማ** ፣፣፩፡፣፣፩። በእርሱ የተቀየሩት በምንም አልከዱም፣ **አልማ** ፳፫፡፣፯። ሺዎችን ወደ እውነት ለማምጣት በእግዚአብሔር እጆች መሳሪያ ስለሆነ ተደሰተ፣ **አልማ** ፳፯፣፡–፡ (አልማ ፳፯)። የአንቲ-ኔፊ-ሌሂ ህዝቦችን መራ፣ **አልማ** ፳፯። ከአልማ ጋር በመገና ኘቱ ታላቅ ደስታ ተሰማው፣ **አልማ** ፳፯፡፣፣፣–፣፡፡።

አሞን፣ የዛራሔምላ ትውልድ። *ደግምም ሊምሂ ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ ከሌሂ-ኔፊ ምድር ወደ ዛራሔምላ ጉዞን የመራ ጠንካራ እና ሀያል ሰው (ሞዛያ ፯፡ ፩–፣፣)። የጥንት ፅሁፎችን አሳዩት እና ባላራዕይ ምን እንደሆነ ገለጸ (ሞዛያ ፡፡ ፣–፣፡)። በኋላም ንጉስ ሊምሒን እና ህዝቦቹን ከላማናውያን ነጻ ለማድረግ እና ወደ ዛራሔምላ መልሶ ለማምጣት ረዳ (ሞዛያ ፳፪)።

አሞፅ

በግምት ከ፯፻፣፣፪ እስከ ፯፻፣፣ ም.ዓ. በአይሁድ ንጉስ ኡዝያ እና በእስራኤል ንጉስ ኢዮርብዓም ዘመናት የተነበየ የብሉይ ኪዳን ነቢይ።

ትንቢተ አሞፅ፣ የብሉይ ኪዳን መፅሐፍ የአሞፅ ትንቢያት እስራኤልን እና ጎረቤቷ አገሮችን ወደ ጽድቅ እንዲመለሱ አስጠንቅቀዋል።

ምዕራፍ ፩–፮ እስራኤልን እና ጎረቤቷ አገሮችን ንስሀ እንዲገቡ ይጠራሉ። ምዕራፍ ፮ ጌታ ምስጢሮቹን ለነብያቱ እንደሚገልፅ እና በመተላለፍ ምክንያት እስራኤል በጠላት እንደምትደመሰስ ያስረዳል። ምዕራፍ ፯–፱ አሶር ከመውረሯ ከብዙ አመቶች በፊት ስለእስራኤል መውደቅ ተነበየ። ምዕራፍ ፱ እስራኤል ወደምድሯ ዳግማ እንደምትመለስ ተነበየ።

አሳ

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የይሁዳ ሶስተኛ ንጉስ። ቅዱሣት መጻህፍት “ልብ ግን በዘመኑ ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ፍጹም ነበረ” ብለው ተፅፈዋል (፩ ነገሥ. ፲፭፡፲፬)። በዘመነ መንግስቱ ጦር ሰራዊትን በብቃት አዘጋጀ፣ የኢትዮጵያን ቀንበር ጣለ፣ የሀሰት ጣኦቶችን አስወጣ፣ እና ህዝቦች ያህዌህን ለመፈለግ ቃል ኪዳን እንዲገቡ ጋበዘ (፩ ነገሥ. ፲፭–፲፮፣ ፪ ዜና ፲፬–፲፮)። ነገር ግን፣ እግሮቹ ሲታመሙ፣ የጌታን እርዳታ አልፈለገም እና ሞተ (፩ ነገሥ. ፲፭፡፳፫–፳፱፣ ፪ ዜና ፲፮፡፲፪–፲፫)።

አሴር

ደግምም እስራኤል፤ ያዕቆብ፣ የይስሐቅ ልጅ ተመልከቱ

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የያዕቆብ እና የልያ ባርያ የዘለፋ ወንድ ልጅ (ዘፍጥ. ፴፡፲–፲፣ ፴)፣ እና ሙሴ የአሴርን ትውልዶች ባረከ (ዘዳግ. ፴፫፡፳–፳፭)። እነዚህ ትውልዶች “ጽኑዓን ኃያላን ሰዎች” ተብለው ተጠርተው ነበር (፩ ዜና ፯፡፴)።

አስሩ ቃላት

ደግምም ሙሴ፤ የእግዚአብሔር ትእዛዛት ተመልከቱ

በነቢዩ ሙሴ በኩል የስነምግባር ጸባይን ለመቆጣጠር እግዚአብሔር የሰጣቸው አስር ቃላት።

በዕብራውያን ቋንቋ የእነዚህ ስም “አስር ቃላት” ነው። እነዚህም ቃል ኪዳን (ዘዳግ. ፬፡፲፫) ወይም ምስክር ተብለው ተጠርተዋል (ዘፀአ. ፳፭፡፳፭፤ ፴፪፡፲፭)። እግዚአብሔር አስሩን ቃላት ለሙሴ እና በእርሱም በኩል ለእስራኤል ሰጠ፣ በዘፀአ. ፲፱፡፱–፳፡፳፣ ፴፪፡፲፣ ፴፬፡፲–፲፱፣ ፴፩፡፩ ውስጥም ተገልጸዋል። ትእዛዛቱ የተቀረጹት በሁለት የድንጋይ ጽላት ላይ ነበር፣ እነዚህም በታቦት ውስጥ ተቀመጡ፤ ከዚህም ጀምሮ ታቦቱ የኪዳን ታቦት ተብለው ተጠርተዋል (ዘኁል. ፲፡፴፫)። ጌታ ከዘዳግ. ፮፡፬–፭ እና ከዘሌዋ. ፲፱፡፲፰ በመጥቀስ አስሩን ቃላት “በሁለቱ ትእዛዛት” አሳጥሮ በማጠቃለል ሰጥቷል (ማቴ. ፳፪፡፴፯–፴፱)።

አስሩ ቃላት በኋለኛው ቀን ራዕያት ውስጥ ደግመው ተሰጥተዋል (ጆ.ስ.ት.፣ ዘፀአ. ፴፬፡፩–፪፣ ፲፬ [ተጨማሪ]፤ ሞሣያ ፲፪፡፴፪–፴፯፣ ፲፫፡፲፪–፳፬፣ ት. እና ቃ. ፵፪፡፲፰–፳፰፣ ፹፱፡፩–፲፫)።

አስሩ ጎሳዎች

እስራኤል ተመልከቱ

አስራት፣ አስራት መክፈል

ደግሞም በኩራት፤ ገንዘብ ተመልከቱ

በቤተክርስቲያን በኩል ለጌታ የሚሰጥ የሰው በአመት አንድ አስረኛ እድገት። የአስራት ገንዘቦች ቤተክርስቲያናትን እና ቤተመቅደሶችን ለመገንባት፣ የሚሰዮን ስራን ለመደገፍ፣ እና የእግዚአብሔርን መንግስት በምድር ላይ ለመገንባት ይጠቀሙባቸዋል።

አብርሐም የንብረቱን ሁሉ አስራት ለመልከጼዴቅ ሰጠ፣ ዘፍጥ. ፲፡፡፲፰–፳ (ዕብ. ፯፡፩–፪፣ ፱፣ አልማ ፲፫፡፲፭)። የምድርም አሥራት ሁሉ የእግዚአብሔር ነው፣ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ነው፣ ዘሌዋ. ፳፯፡፴–፴፡፡ ከዘርህ ፍሬ ሁሉ አሥራት ታወጣለህ፣ ዘዳግ. ፲፡፡፳፪፣ ፳፫፡ የሁሉንም አሥራት አብዝተው አቀረቡ፣ ፪ ዜና ፴፩፡፭ ሰው እግዚአብሔርን ይሰርቃልን? እናንተ ግን እኔን ሰርቃችኋል። እናንተም። የሰረቅንህ በምንድር ነው? ብላ ችኋል። በአሥራትና በበኵራት ነው፣ ሚል. ፫፡፰–፲፩ (፫ ኔፊ ፳፬፡፰–፲–፲፩)።

አስራትን የሚከፍልም በሚመጣበት ጊዜ አይ ቃጠልም፣ ት. እና ቃ. ፭፬፡፳፫ (ት. እና ቃ. ፻፲፭፡፫)። የጌታ ቤት በህዝቦቹ አስራት ይሰራ፣ ት. እና ቃ. ፻፲፡፲፩–፲፪። ጌታ የአስራት ህግን ገለጸ፣ ት. እና ቃ. ፻፲፱። አስራት በሽንጎ ይከፋፈላል፣ ት. እና ቃ. ፻፳፡

አስቀድሞ መወሰን

ቀድሞ መመረጥ ተመልከቱ

አስተዳደሪያዊ አዋጅ ፩

ደግሞም መግለጫ፤ ውድሩፍ፣ ውልፈርድ፤ ጋብቻ፣ መጋባት—ከአንድ ሚስት በላይ ማግባት ተመልከቱ

በትምህርት እና ቃል ኪዳኖች በመጨረሻ ገጾች ላይ የታተሙት፣ የአስተዳደሪያዊ አዋጅ ፩ የመጀመሪያ ክፍል መግለጫም ተብሎ ይታወቃል። የተሰጠውም በፕሬዘደንት ውልፈርድ ውድሩፍ ነበር እናም በጥቅምት ፯፣ ፲፰፻፶፯ (እ.አ.አ.) በአጠቃላይ ጉባኤ ውስጥ ለቤተክርስቲያኗ አባላት ቀረበ። ከ፲፰፻፶፰ (እ.አ.አ.) ጀምሮ፣ የተለያዩ ህግጋት በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ከአንድ ሚስት በላይ ማግባትን ህገወጥ አደረጉት። ጌታ በራዕይ ከአንድ ሚስት በላይ ማግባትን ካላቆሙ በቅዱሳን ላይ ምን እንደ ሚደርስ ለውልፈርድ ውድሩፍ አሳየ። መግለጫው

ከአንድ ሚስት በላይ ማጋባት እንደቆመ ማስታወቂያ ሰጠ።

አስተዳደሪያዊ አዋጅ ፪። *ደግምም* ኪምባል፣ ስፔንሰር ደብሊው፤ *ክህነት ተመልከቱ*

አሁን በትምህርት እና ቃል ኪዳኖች በመጨረሻ ገጾች ላይ የታተሙት፣ ማን ክህነትን ለመያዝ እንደሚችል በሚመለከት የተሰጠ የትምህርት መረጃ። በሰኔ ፲፱፻፹፫ (እ.አ.አ.)፣ ጌታ ክህነት ለቤተክርስቲያና ብቁ አባላት በሙሉ እንዲሰጥ ለፕሬዘደንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምባል ገለጸ። ይህም የቆዳ ቀለማቸውንም ይሁን ዘራቸውን ሳይመለከት ክህነትን ብቁ ለሆኑ ወንዶች ለመስጠት እና የቤተመቅደስ በረከቶችንም ብቁ ለሆኑ አባላት በሙሉ ለመስጠት የሚቻል አስደረገ። በመስከረም ፴፣ ፲፱፻፹፯ (እ.አ.አ.)፣ ይህ አዋጅ ለቤተክርስቲያኗ አጠቃላይ ጉባኤ ቀርቦ ነበር እናም ባንድ ድምፅ ተቀባይነት አገኘ።

አስቴር

ታላቅ እምነት የነበራት እና በመፅሐፈ አስቴር ውስጥ ዋና ባለታሪክ።

መፅሐፈ አስቴር፣ ህዝቦቿን ከጥፋት ለማዳን ንግስት አስቴር የነበራት ታላቅ ብርቱነትን የሚያሳይ በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚገኝ መፅሐፍ።

ምዕራፍ ፩–፪ የአይሁዳ ሴትና መርዶክዮስ የሚባለው የአይሁዳ ሰው በጉዲፈቻ ያሳድጋት የነበረችው ሴት ልጅ በውበቷ ምክንያት የፋርስ ንግስት እንድትሆን እንዴት እንደተመረጠች ይነግራሉ። *ምዕራፍ ፫* በንጉሱ ቤት ዋና አለቃ የነበረው ሀማን መርዶክዮስን እንደጠላና የአይሁዳ ህዝቦችን በሙሉ ለመግደል አዋጅ እንዳገኘ ይገልጻል። *ምዕራፍ ፬–፮* አስቴር፣ እራሷን በአደጋ ላይ በመጣል፣ ዜግነቷን ለንጉሱ እንዴት እንደገለጸችና የአዋጁን ለውጥ እንዳመጣች ይናገራሉ።

አስጸያፊ፣ አስከፊ፣ አሰቃቂ፣ ርኩሰት። *ደግምም ኃጢያት ተመልከቱ*

በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ፣ ለጻድቅ እና ንጹሁ ጽያፊ እና ጥላቻ የሚያመጣ።

ውሸተኛ ከንፈር በእግዚአብሔር ዘንድ አሰጸያፊ ነው፣ *ምሳ.* ፲፪፡፳፪።

ኩራት በጌታ ፊት የርኩሰት ነው፣ *ያዕቆ.* ፪፡፲፫–፳፪። ክፉዎች በራሳቸዉ እርኩሰት ሁኔታ ይመደባሉ፣ *ሞዛያ* ፫፡፳፭። ንጹህ አለመሆን ደም ከማፍሰስ ወይንም መንፈስ ቅዱስን ከመካድ በቀር ከሌሎች ኃጢአቶች ሁሉ ይበልጥ አስከፊ ነው፣ **አልማ** ፴፱፡፣–፴።

የጌታ ቁጣ በርኩሰታቸው ላይ ተቀጣጥሏልና፣ *ት. እና ቃ.* ፶፯፡፳፡።

አሶር

በብሉይ ኪዳን ዘመናት ውስጥ በሙሉ፣ ከተወዳዳሪዋ ባብሎን ጋር፣ ሶርያን እና ፍልስጥኤምን የገዛች የጥንት ግዛት። ምንም እንኳን አሶራውያን ከ፲፪ኛው ሺህ ም.ዓ. ግማሽ እስከ ፯ኛው ሺህ ም.ዓ. መጨረሻ ድረስ ታላቅ ሀይል የነበሩ ቢሆኑም፣ የረጋ የፖለቲካ ድርጅት ለመገንባት በምንም አልቻሉም ነበር። በፍርሀት፣ ጠላቶቻቸውን በእሳት እና በጎራዴ በመደምሰስ ወይም የጠላቶቻቸውን ህዝቦች ታላቅ ክፍልን ወደ ግዛቶቻቸው ሌላ ክፍሎች በመላክ ደካማ እንዲሆኑ በማድረግ ይገዙ ነበር። በአሶራውያን ተገዢነት ስር የነበሩት ህዝቦች ከመንግስት ጋር ሁልጊዜም ይታገሉ ነበር። (፪ ነገሥ. ፲፰–፲፱፣ ፪ ዜና ፴፪፣ ኢሳ. ፯፡፲፯–፳፣ ፲፣ ፲፱፣ ፴፯ ተመልከቱ።)

አርማጌዶን። *ደግምም ማጎግ፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት፣ ጎግ ተመልከቱ*

የአርማጌዶን ስም “የሚጎዶ ተራራ” የሚል ትርጉም ካለው ከእብራውያን *ሀር ሚጎዶ* መንጭ የመጣ ነው። የሚጎዶ ሸለቆ በኤስድራኤሎን ሜዳ ምስራቃዊ ክፍል ውስጥ፣ ከሰሜን ኢየሩሳሌም ሀምሳ ኪሎ ሜትር አልፎ ያለ ነው፣ እና በብሉይ ኪዳን ጊዜዎች ብዙ በጣም ወሳኝ የሆኑ ጦርነቶች የነበረበት ቦታ ነው። በጌታ ዳግም ምፅዓት ቅርብ ጊዜ የሚመጣው ታላቅ እና የመጨረሻው ጦርነት የአርማጌዶን ጦርነት የሚባልበት ምክንያት በዚያ አካባቢ ስለሚጀምር ነው። (ሕዝ. ፴፱፡፲፩፣ ዘካ. ፲፪–፲፬፣ በልዩም ፲፪፡፲፩፣ ራዕ. ፲፮፡፲፬–፳፩።)

አሮናዊ ክህነት። *ደግምም* አሮን፣ የሙሴ ወንድም፤ *ክህነት*፤ *የሙሴ ህግ ተመልከቱ*

አነስተኛው ክህነት (ዕብ. ፯፡፲፩–፲፪፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፲፣–፲፱)። ሀላፊነቶቹም ኤጲስ ቆጶስ፣ ካህን፣ አስተማሪ፣ ዲያቆን ናቸው (ት. እና ቃ. ፴፬፡፴፣ ፲፯፡፲፣ ፲፱–፲፭፣ ፴፯–፴፰)። በጥንት፣ በሙሴ ህግ በታች፣ ሊቀ ካህናት፣ ቄሶች፣ እና ሌዋውያኖች ነበሩ። የጥንት እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ላይ ስላመጹ፣ ሙሴ እና ቅዱስ ክህነት ከእነርሱ ተወሰዱ እናም አነስተኛው ክህነት ቀጠለ። ለመቀደስ እና የመልከ ጼዴቅ ክህነትንና ስነስርዓቶቹን ለመቀበል እምቢ ብለው ነበር። (ት. እና ቃ. ፴፬፡፳፡፳፫–፳፮ ተመልከቱ።) የአሮናዊ ክህነት በጊዜአዊ እና በህግ እና ወንጌል ውጪአዊ ስርዓቶችን ያስተዳድራል (፩ ዜና ፳፫፡፳፯–፴፪፣ ት. እና ቃ. ፴፬፡፳፡፳፮–፳፯፣ ፲፯፡፲፣ ፴)። የመልአክትን አገልግሎት፣ እና የንስሃ ወንጌልን እና የመጥመቅ ቁልፎችን ይዟል (ት. እና ቃ. ፲፫)። የአሮናዊ ክህነት በዚህ ዘመን ፍጻሜ ላይ በ፲፭ ግንቦት ፲፰፻፹፭ (እ.አ.አ.) ወደ ምድር ደግሞ ተመለሰ። መጥምቁ ዮሐንስ በሀርመኒ፣ ፔንስልቬንያ፣ አጠገብ ይህን

በጀሴፍ ስሚዝ እና በኦሊቨር ካውደሪ ላይ አረጋ ገጠ (ት. እና ቃ. ፲፫፣ ጀ.ስ.—ታ. ፩፡፳፰–፳፱)።

ለእርሱም ለዘላለም ክህነት ቃል ኪዳን ይሆን ለታል፣ ዘኁል. ፳፭፡፲፫። የሌዊንም ልጆች ያጠ ራል፡ ያነጥራቸዋልም፣ ሚል. ፫፡፫ (፫ ኔፊ ፳፬፡፫)።

ማንም ክብሩን ለራሱ የሚወስድ የለም፣ ዕብ. ፭፡፬። በሌዊ ክህነት ፍጹምነት አይመጣም፣ ዕብ. ፯፡፲፩።

የሌዊ ልጆች እንደገና መሰዋዕት ለጌታ እስኪያ ቀርቡ ድረስ ክህነት ከምድር ላይ ዳግመኛ በፍጹም አይወሰድም፣ ት. እና ቃ. ፲፫። ጀሴፍ ስሚዝ እና ኦሊቨር ካውደሪ በአሮናዊ ክህነት ተሹመው ነበር፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፡ ፳። አነስተኛው ክህነት የመል አክትን አገልግሎት ቁልፍ ይዟል፣ ት. እና ቃ. ፲፱፡፳፯፲፮ (ት. እና ቃ. ፲፫)። በስም መልክ ጴጴቅ እና አሮናዊ የሚባሉ፣ ሁለት የክህነት ባለስልጣኖች አሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፩። ሁለተኛው ክህነት አሮ ናዊ ክህነት ተብሎ ይጠራል፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፲፫።

አሮን፣ የሙሴ ወንድም። *ደግሞም ሙሴ፤ አሮናዊ ክህነት ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የሌዊ ነገር የእንበረምና የዮካብድ ወንድ ልጅ (ዘፀአ. ፮፡፲፯–፳)፤ የሙሴ ታላቅ ወንድም (ዘፀአ. ፯፡፯)።

የእስራኤል ልጆችን ከግብፅ ለማምጣት ሙሴን እንዲረዳ እና የእርሱ ቃል ተቀባይ እንዲሆን በጌታ ተመድቦ ነበር፣ ዘፀአ. ፬፡፲–፲፯፣ ፳፯–፴፩፣ ፭፡፩–፲፪፡፲፩። በሲና ተራራ ላይ፣ ሙሴ ስለአሮንና አራት ወንዶች ልጆቹ ወደ አሮናዊ ክህነት መመደብ መመ ሪያ ተቀበለ፣ ዘፀአ. ፳፰፡፩–፬። ህዝቦች ስለጠየቁት የወርቅ ጥጃ ሰራ፣ ዘፀአ. ፴፪፡፩–፮፣ ፳፭፣ ፴፬፣ ፴፭። በየ፳፫ኛ አመቱ በሆር ተራራ ላይ ሞተ፣ ዘኁል. ፳፡፳፫–፳፱ (ዘኁል. ፴፫፡፡ ፴፰–፴፱)።

ጌታ ክህነትን በአሮን እና በዘሩ ላይ አረጋገጠ፣ ት. እና ቃ. ፲፬፡፡ ፲፰፣ ፳፯–፳፰፣ ፴። የክህነት ጥሪ ያቸውን የሚያጎሉ የሙሴ እና የአሮን ልጆች ይሆ ናሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፬፡፡ ፴፫–፴፴።

አሮን፣ የሞዛያ ልጅ። *ደግሞም ሞዛያ፣ የቢንያም ልጅ፣ የሞዛያ ልጆች ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ የንጉስ ሞዛያ ወንድ ልጅ አሮን በሚስዮን ሲያገለግል ትጉህ ጥረቱ ብዙ ነፍሶችን ወደ ክርስቶስ ቀየር።

ቤተክርስትያኗን ለማጥፋት የፈለገ የማያምን ነበረ፣ ሞዛያ ፳፯፡፡ ፳–፲፣ ፴፩። ለእርሱና አብ ረውት ለነበሩት መላእክት ታያቸው፣ ሞዛያ ፳፯፡፲፩። ንስሀ ገባ እና የእግዚአብሔርን ቃል መስበክ ጀመረ፣ ሞዛያ ፳፯፡፴፪–፳፳፡ ፳። እንደ ንጉስ ለመመደብ እምቢ ብሎ እና ወደላማናው ያን ምድር የእግዚአብሔርን ቃል ለመስበክ ሄደ፣ አልማ ፲፯፡፮–፱። ለመመሪያ ጾመም ጸለየም፣ አልማ ፲፯፡ ፳–፲፩። የንጉስ ላሞኒህ አባትን አስ ተማረ፣ አልማ ፳፪፡፩–፳፯። ለዞራማውያን ለመ ስበክ ሄደ፣ አልማ ፴፩፡፮–፯።

አቡቃለምሲስ። *ደግሞም የዮሐንስ ራዕይ ተመልከቱ*

የአዲስ ኪዳን የመጨረሻው መፅሐፍ፣ የራ ዕይ መፅሐፍ፣ ማንኛውም ትርጉም ያለው ራዕይ ማለትም ሊሆን ይችላል፣ ከግሪክ ቃል “የተገለጸ” ወይም “የተገለጠ” ማለት ነው።

አቢናዲ። *ደግሞም ሰማዕት፣ ሰማዕትነት ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ የኔፋውያን ነቢይ።

ንስሀ ካልገቡ እግዚአብሔርን የክፉን ንጉስ ኖኅን ህዝቦች እንደሚቀጣ ተነበየ፣ ሞዛያ ፲፩፡፳–፳፭። የንጉስ ኖኅን እና የህዝቦቹን መደምሰስ ስለተነበየ ታሰረ፣ ሞዛያ ፲፪፡፩–፲፯። የንጉስ ኖኅን ክፉ ቁሶች ስለሙሴ እና ስለክርስቶስ ህግ አስተማረ፣ ሞዛያ ፲፪–፲፯። ሽማግሌው አልማ አመነው እና ቃላቶቹን ጻፈ፣ ሞዛያ ፲፯፡፪–፴። በንጉስ ኖኅ በእሳት ተገ ደለ፣ ሞዛያ ፲፯፡፳።

አቤል። *ደግሞም ቃየን፣ አዳም ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የአዳም እና የሔዋን ልጅ።

ለእግዚአብሔር ከወንድሙ ቃየን ካደረገው ይልቅ እጅግ በጣም ጥሩ የሆነ መስዋዕት አቀረበ፣ ዘፍጥ. ፬፡፡ ፬–፭ (ዕብ. ፲፩፡፡ ፬፣ ሙሴ ፭፡ ፲፯–፳፩)። በቃየን ተገደለ፣ ዘፍጥ. ፬፡ ፰ (ሙሴ ፭፡ ፴፪)።

ክህነትን ከአዳም ተቀበለ፣ ት. እና ቃ. ፲፬፡፡ ፲፯።

ሰይጣን ከቃየን ጋር አቤልን ለመግደል የሚስጥር እቅድ ሰራ፣ ሙሴ ፭፡ ፳፰–፴፩ (ሔስ. ፮፡ ፳፯)።

አብራም። *አብርሐም ተመልከቱ*

አብርሐም። *ደግሞም የአብርሐም ቃል ኪዳን ተመልከቱ*

ከለዳውያን ዑር ውስጥ የተወለደ፣ የታራን ወንድ ልጅ (ዘፍጥ. ፲፩፡፡ ፳፯፣ ፴፩፣ ፲፯፡፡ ፳)። የምድር ህዝ ቦች ሁሉ የሚባረኩበት ዘለአለማዊ ቃል ኪዳን ጌታ የገባለት የጌታ ነቢይ። አብርሐም በመጀመሪያ አብ ራም ተብሎ ይጠራ ነበር።

ወደ ሐራን ተሰደደ፣ በዛም ታራን ሞተ፣ ዘፍጥ. ፲፩፡ ፴፩–፴፪ (አብር. ፪፡ ፩–፳)። ወደ ከነዓን እን ዲጓዝ እና መለኮታዊ ቃል ኪዳን እንዲቀበል በእ ግዚአብሔር ተጠራ፣ ዘፍጥ. ፲፪፡ ፩–፳ (አብር. ፪፡ ፱፣ ፲፭–፲፯)። ወደ ግብፅ ተጓዘ፣ ዘፍጥ. ፲፪፡ ፱–፳ (አብር. ፪፡ ፳፩–፳፭)። በኬብሮን ውስጥ ሰፈረ፣

ዘፍጥ. ፲፫፡፲፰። ሎጥን አዳነ፣ ዘፍጥ. ፲፱፡፩–፲፯። ከመልከ ጼዴቅ ጋር ተገናኘ፣ ዘፍጥ. ፲፱፡፲፰–፳። አጋር ልጁን እስማኤልን ወለደች፣ ዘፍጥ. ፲፯፡፲፭–፲፯። ስሙ ወደ አብርሐም ተቀየረ፣ ዘፍጥ. ፲፯፡፩። ጌታ አብርሐም እና ሳራ ወንድ ልጅ እንደሚወልዱ ነገራቸው፣ ዘፍጥ. ፲፯፡፲፭–፳፪፣ ፲፰፡፩–፲፩። ሳራ ወንድ ልጁን ይስሐቅን ወለደች፣ ዘፍጥ. ፳፩፡፪–፫። ይስሐቅን እንዲሰዋ ታዘዘ፣ ዘፍጥ. ፳፪፡፩–፲፰። ሳራ ሞተች እና ተቀበረች፣ ዘፍጥ. ፳፫፡፩–፪፣ ፲፱። አብርሐም ሞተ እና ተቀበረ፣ ዘፍጥ. ፳፭፡፰–፲።

አብርሃም ይስሀቅን ለመስዋዕት በማቅረብ ታዛዥ ነቱ የእግዚአብሔርና ከአንድያ ልጁ ጋር አምሳልነት ያለው ነው፣ ያዕቆ. ፡፡፡–፡፡ ለመልከ ጼዴቅ አስራት ከፈለ፣ አልማ ፲፫፡፲፭። የክርስቶስ መምጣትን አስ ቀድሞ ተመለከተም መሰከረም፣ ሔለ. ፡፡፡፲፭–፲፯።

ክህነትን ከመልከ ጼዴቅ ተቀበለ፣ ት. እና ቃ. ፡፡፡–፡፡። ታማኝ የአብርሐም ዘር ይሆናል፣ ት. እና ቃ. ፡፡፡–፡፡ (ገላ. ፫፡፳፯–፳፱)። ሁሉ ንም ነገሮች በራዕይ ተቀበለ እናም ዘለአለማዊነትን ተቀብሏል፣ ት. እና ቃ. ፡፡፡–፡፡።

የአባቶችን በርከቶች እና የክህነት ምደባን ፈለገ፣ **አብር.** ፩፡፩–፡፡። በከላውዴዎ የሀሰት ቁሶች ተሰ ደደ፣ **አብር.** ፩፡፩–፲፭። በጌታ ዳነ፣ **አብር.** ፩፡፲፯–፳። ስለጸሀይ፣ ጨረቃ፣ እና ኮከቦች ተማረ፣ **አብር.** ፫፡፩–፲፡። ስለምድር በፊት ህይወት እና ፍጥረት ተማረ፣ **አብር.** ፫፡፳፪–፳፳።

መፅሐፈ አብርሐም፣ በ፲፳፻፡፳ (እ.አ.አ.) ወደ ቤተክርስቲያኗ እጅ የገባ በአብርሐም የተጻፈ የጥ ንት መዝገቦች። መዝገቦቹ እና አንዳንድ አስከሬ ኖች በግብፅ መቃብሮች ውስጥ በአንቶኒዮ ሌቦሎ ተገኝተው ነበር፣ እነዚህንም ለማይክል ቻንድለር በኑዛዜ ቃል ተወለት። በ፲፳፻፡፳ (እ.አ.አ.) ቻንድ ለር እነዚህን በዩናትድ ስቴት ውስጥ ለእይታ አቀ ረባቸው። አንዳንድ የጀሴፍ ስሚዝ ጓደኞች ገዙአ ቸው እና ለነብዩ ሰጡት፣ እርሱም ተረጎማቸው። ከእነዚህ አንዳንድ ፅሁፎችም በየታላቅ ዋጋ ዕንቁ ውስጥ ይገኛሉ።

ምዕራፍ ፩ አብርሐም ክፉ ቁሶች ሊሰዉት በሞ ከሩበት በከላውዴዎ ዑር ውስጥ ስለነበረው አጋ ጣሚዎች ይመዘግባል ምዕራፍ ፪ ስለከነዓን ጉዞው ይናገራል። ጌታም ታየው እና ቃል ኪዳን ከእርሱም ጋር ገባ። ምዕራፍ ፫ አብርሐም ሁለንተናን እንዳየ እና በሰማያዊ ሰውነቶች መካከል ያለውን ግንኙነ ቶች እንደተመለከተ መዝግቧል። ምዕራፍ ፡፡–፡ የፍ ጥረት ሌላ መዝገቦች ናቸው።

የአብርሐም ዘር፣ ለህግጋት እና ኢየሱስ ክርስ ቶስ ወንጌል ስነስርዓቶች ታዛዥ በመሆን እግዚአ ብሔር ለአብርሐም የገባውን የተስፋ ቃላትና ቃል ኪዳኖች የሚቀበሉ ህዝቦች። ወንዶች እና ሴቶች የእውነት የአብርሐም ዝርያ ከሆኑ ወይም ወንጌልን በመቀበል እና በመጠመቅ ወደ ቤተሰቡ በጉዲፈቻ ከተወሰዱ እነዚህን በረከቶች ይቀበላሉ (ገላ. ፫፡፳፯–፳፱፣ ፡፡፡–፡፡፣ ት. እና ቃ. ፡፡፡–፡፡፣ ፡፡፡–፡፡፣ ፡፡፡–፡፡፣ ፡፡፡–፡፡)። ለአብርሐም የእ ውነት ዘሮች በረከቶቻቸውን ታዛዥ ባለመሆን ለማ ጣት ይችላሉ (ሮሜ ፡፡፡፣ ፡፡–፡–፡)።

አብደናጎ። *ደግሞም ዳንኤል ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሲድራቅ፣ ሚሳቅ፣ እና አብደናጎ ከዳንኤል ጋር ወደ ባቢሎን ንጉስ ናቡከደነፆር ቤተመንግስት የተወሰዱ ሶስት የእስ ራኤል ወጣቶች ነበሩ። የአብደናጎ ዕብራውያን ስም ዓዛርያስ ነበር። አራቱ ወጣት ሰዎች የንጉሱን ስጋ እና ወይን በመብላት እና በመጠጣት እራሳቸውን ለመበከል እምቢ አሉ (ዳን. ፩)። ሲድራቅ፣ ሚሳቅ፣ እና አብደናጎ ወደሚነደው ወደ እቶን እሳት ተጣሉ ነገር ግን በእግዚአብሔር ልጅ በተአምራት ተጠብ ቀው ነበር (ዳን. ፫)።

አብድዩ

ስለኤዶም መጥፋት አስቀድሞ የተናገረ የብ ሉይ ኪዳን ነቢይ። የተነበየው ምናልባት ኢዮራም በነገሰበት ጊዜ (፳፻፵፯–፳፻፵፭ ም.ዓ.) ወይም በ፳፻፲፮ ም.ዓ. ውስጥ ባቢሎን በወረረችበት ጊዜ ነበር።

ትንቢተ አብድዩ፣ የብሉይ ኪዳን መፅሐፍ። አንድ ምዕራፍ ብቻ ነበረው። በውስጡም፣ አብ ድዩ ስለኤዶም መጥፋት ጻፈ እናም በፅዮን ተራራ ላይ አዳኞች እንደሚቆሙ ተነበየ።

አንቲ-ኔፊ-ሌሂ። *ደግሞም* አሞን፣ የሞዛያ ወንድ ልጅ፣ የሔለማን ልጆች፣ የሞዛያ ልጆች *ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ በሞዛያ ወንድ ልጆች ለተቀየሩ ላማናውያን የተሰጠ ስም። ከተቀ የሩ በኋላ፣ እነዚህ የአሞን ህዝቦች ተብለው የተጠሩ ህዝቦች በህይወቶቻቸው በሙሉ ታማኝ ነበሩ (አልማ ፳፫፡፱–፣ ፲፭–፲፯፣ ፳፯፡፳–፳፰)።

አንቲ-ኔፊ-ሌሂዎች የሚል ስም ወሰዱ፣ **አልማ** ፳፫፡፲፭–፲፯፣ ፳፱፡፩። ደም ለማፍሰስ እምቢተ ኞች ሆኑ እናም የጦር መሳሪያዎቻቸውን ቀበሩ፣ **አልማ** ፳፱፡፯–፣ ፲፱። ልጆቻቸው ለጦርነት ተዘጋጁ እናም ሔለማንን እንደ መሪያቸው መረጡ፣ **አልማ** ፶፫፡፲፭–፲፱፣ ፶፭–፶፰። (ደግሞም እነዚህ ፳፪ ወጣት ጦረኞች ተብለው ይታወቃሉ።)።

አንደበት። ምላስ *ተመልከቱ*

አንድ። አንድነት፣ እግዚአብሔር፣ አምላክ *ተመልከቱ*

የቅዱሳት መጻህፍት መመሪያ

አንድ ሺህ አመት ፯፲

አንድ ሺህ አመት። *ደግምም ሲያል፤ የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት ተመልክቱ*

ክርስቶስ በምድር ላይ ለመንገስ በሚመጣበት ጊዜ የሚጀምረው የ አንድ ሺህ አመት ጊዜ (እ.አ. ፩፡፲)።

ሕዝብም በሕዝብ ላይ ሰይፍ አያነሣም፥ ሰልፍም ከእንግዲህ ወዲህ አይማሩም፣ ኢሳ. ፪፡፬ (ሚክ. ፬፡፫፣ ፪ ኔፊ ፲፪፡፬)። ባድማ የነበረች ይህች ምድር እንደ ዔድን ገነት ሆናለች፣ ሕዝ. ፴፮፡፴፭።

ከክርስቶስም ጋር ሺህ ዓመት ኖሩና ነገሡ፡ ራዕ. ፳፡፬።

በህዝቦቹ ፅድቅ ምክንያት ሰይጣን ኃይል የለ ውም፣ ፩ ኔፊ ፳፪፡፳፯።

በጽድቅም ከሰዎች ጋር በምድር ላይ ለአንድ ሺ አመታት እኖራለሁ፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፲፩። አንድ ሺ አመት ሲጠናቀቅ፣ መሬትን የምተዋት ለትንሽ ጊዜ ይሆናል፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፳፪። ታላቁ አንድ ሺህ ዘመን ይመጣል፣ ት. እና ቃ. ፸፫፡፴። ልጆችም ወደ ደህንነት ያለሀጢያት ያድጋሉ፣ ት. እና ቃ. ፸፭፡፻፳። ልጆች እድሜአቸው እስኪገፋ ድረስም ያድጋሉ፣ ሽማግሌዎችም በቅጽበት ዓይንም ይቀ የራሉ፣ ት. እና ቃ. ፳፫፡፻፩። በሰባት ሺ አመቶች መጀመሪያ ላይ ጌታ አምላክ ምድርን ይቀድሳል፣ ት. እና ቃ. ፫፯፡፲፪። ይህ ሺህ ዓመት እስኪፈ ጸም ድረስ፣ በሕይወት አይኖሩም፣ ት. እና ቃ. ፲፫፡፻፩። ሰይጣንም ለአንድ ሺህ ለሚሆን ዘመ ንም አይፈታም፣ ት. እና ቃ. ፲፫፡፻፲። አንድ ሺህ አመት በግልፅ ተዘርዝሯል፣ ት. እና ቃ. ፻፩፡፳፫–፴፩።

ለአንድ ሺ አመቶችም ምድር ታርፋለች፣ ሙሴ ፯፡፳፬፡፩።

አንድነት። *ደግምም እግዚአብሔር፣ አምላክ ተመልክቱ*

በሀሳብ፣ በፍላጎት፣ እና በአላማ በመጀመሪያ ከሰማይ አባታችንና ከኢየሱስ ጋር፣ እና ከእዚያም ከሌሎች ቅዱሳን ጋር አንድ መሆን።

ወንድሞች በኅብረት ቢቀመጡ መልካም ነው፣ መዝ. ፻፴፫፡፩።

እኔና አብ አንድ ነን፣ ዮሐ. ፲፡፴ (ት. እና ቃ. ፶፡፳፫)። ኢየሱስ እርሱ እና አባቱ አንድ እንደሆኑ ሁሉም አንድ እንዲሆኑ ጸለየ፣ ዮሐ. ፲፯፡፲፩–፳፫ (፫ ኔፊ ፲፱፡፳፫)። ሁላችሁ የተባበራችሁ እንድት ሆኑ እንጂ መለያየት በመካከላችሁ እንዳይሆን እለ ምናችኋለሁ፣ ፩ ቆሮ. ፩፡፲።

በአንድ ሀሳብና በአንድ ልብ ሁኑ፣ በሁሉ ነገ ሮች ተስማሙ፣ ፪ ኔፊ ፭፡፳፭። ቅዱሳን ልባቸው በአንድ ላይ በአንድነት ይጣበቁ፣ ሞዛያ ፲፰፡፳፭። ኢየሱስ በኔፋውያን ደቀ መዛሙርት መካከል አንድ ነት እንዲኖር ጸለየ፣ ፫ ኔፊ ፲፱፡፳፫። ደቀ መዛሙ ርቱ በብርቱ ፀሎታቸው እና ያማቸው አንድ ሆነው ነበር፣ ፫ ኔፊ ፳፯፡፩።

አብ፣ ወልድ፣ እና መንፈስ ቅዱስ አንድ ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፳፡፳፯–፳፰ (ት. እና ቃ. ፴፭፡፪፣ ፻፡፻፫)። ከእውነት ቤተክርስቲያን ጋር አንድ መሆን ሀላፊነታችሁ ነው፣ ት. እና ቃ. ፳፫፡፯። እንደ ትእ ዛዜ በጸሎት አንድ ሆናችሁ በእምነት የምትጠይ ቁትን ማንኛውንም ትቀበላላችሁ፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፮። አንድ ካልሆናችሁ የእኔ አይደላችሁም፣ ት. እና ቃ. ፴፰፡፳፯።

እነርሱ የአንድ ልብ እና የአንድ አእምሮ ስለ ነበሩ፣ ጌታ ህዝቡን ፅዮን ብሎ ጠራቸው፣ ሙሴ ፯፡፲፰።

አንድያ ልጅ። *ደግምም መወለድ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልክቱ*

የኢየሱስ ክርስቶስ ሌላ ስም። እርሱ የአብ አንድያ ልጅ ነው (ሉቃ. ፩፡፳፯–፴፭፣ ዮሐ. ፩፡፲፬፣ ፫ ፡፲፣ ፩ ኔፊ ፲፣ ፲፡–፳፣ ፪ ኔፊ ፳፭፡፲፬፣ አልማ ፯፡፲፣ ፲፪፡፴፫፣ ሙሴ ፯፡፳፪)።

አዕምሮ

የአዕምሮ ሀይል፣ የህሊና ሀሳብ ሀይሎች።

በፍጹም ልብና በነፍስህ ፈቃድም አምልከው፣ ፩ ዜና ፳፰፡፱፡፪።

ጌታ አምላክህን በፍጹም ነፍስህም ውደድ፣ ማቴ. ፳፪፡፴፯።

ስለ ዓለም ማሰብ ሞት እንደሆነና፣ ስለመንፈሳዊ ነገር ማሰብ ዘለዓለማዊ ህይወት ነው፣ ፪ ኔፊ ፱፡፴፱። የጌታ ድምፅ በአዕምሮዬ መጣ፣ ኢኖስ ፩፡፲። ቃሉ ታላቅ ዝንባሌ ስላለው ከጎራዴ የበለጠ በአዕምሮ አቸው ላይ ውጤት ይኖረዋል፣ አልማ ፴፭፡፪፡፫።

በአዕምሮህ እነግርሃለሁ፣ ት. እና ቃ. ፳፡፪። በአ እምሮህ ውስጥ ልታጠናው ይገባል፣ ት. እና ቃ. ፱፡፳። የዘለአለም ማስተዋልም በአዕምሮዎቻችሁ ላይ ይረፉ፣ ት. እና ቃ. ፶፫፡፴፩። ከዚህ በፊት አዕምሮአችሁ ጨልሞባችሁ ነበር፣ ት. እና ቃ. ፲፫፡፲፡፲፩። ወደ መኝታችሁ በጊዜ ሂዱ፣ ሰውነቶቻ ችሁ እና አዕምሮዎቻችሁ እንዲነቃቁ ዘንድ በማ ለዳም ተነሱ፣ ት. እና ቃ. ፲፫፡፻፳፩።

ሰይጣን የእግዚአብሔርን ሀሳብ አያውቅም፣ ሙሴ ፩፡፮። እነርሱ አንድ ልብ እና አንድ አእ ምሮ ስለነበሩ፣ ጌታ ህዝቡን ፅዮን ብሎ ጠራቸው፣ ሙሴ ፯፡፲፰።

አክሊል። *ደግምም የዘለዓለም ህይወት ተመልክቱ*

በመሪዎች ጭንቅላት ላይ የሚቀመጥ ክብ ጌጣጌጥ። ይህም የሰለስቲያል ሀይል፣ ግዛት፣ እና አምላክነት ምልክት ሊሆንም ይችላል። የእግዚአብ ሔርን ትእዛዛት ሁሉ በማክበር የሚጸኑት የዘለአለም

ህይወት ዘውድን ይቀበላሉ። (ት. እና ቃ. ፳፡፲፡፡ ሙሴ ፯፡፹፯፤ ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፡፩ ተመልከቱ።)

ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፣ ፪ ጢሞ. ፬፡፰። የማያልፈውን የክብርን አክሊል ትቀበላላችሁ፣ ፩ ጴጥ. ፭፡፬።

በእኔ የሞቱት ሙታን የጽድቅን አክሊል ይቀበላሉ፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፲፫። በአባቴ ቤት ውስጥ አክሊል ይቀበላሉ፣ ት. እና ቃ. ፹፱፡፪። ጌታ ቅዱሳንን ለተዘጋጀላቸው አክሊል እንዲመጡ ያዘጋጃቸዋል፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፲፭። ጌታ ለቅዱሳኑ በቀኝ እጁ በኩል የክብር አክሊል ኪዳን ገብቶላቸዋል፣ ት. እና ቃ. ፲፬፡፲።

አክዓብ። *ደግምም ኤልዛቤል ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የሰሜን እስራኤል ከሁሉም በላይ ክፉ እና ሀይለኛ ንጉስ ከሆኑት አንዱ። የሲዶንን ልዕልት ኤልዛቤልን አገባ፣ በእርሷም ተፅዕኖ በኩል የበኣልን እና የአስታሮት ማምለክን በእስራኤል ውስጥ መሰረተ (፩ ነገሥ. ፲፮፡፳፱–፴፫፣ ፪ ነገሥ. ፫፡፪)፡ እና ነብያትን እና ያህዌህን ማምለክ ለማስወገድ ጥረት ተደርጎ ነበር (፩ ነገሥ. ፲፰፡፲፫)።

በእስራኤል ላይ በሰማሪያ ሀያ ሁለት ዓመት ነገሠ፣ ፩ ነገሥ. ፲፮፡፳፱ (፩ ነገሥ. ፲፮–፳፪)። ከእርሱ በፊት ከነበሩት ሁሉ ይልቅ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ አደረገ፣ ፩ ነገሥ. ፲፮፡፴። በጦርነትም ተገደለ፣ ፩ ነገሥ. ፳፪፡፳፱–፴።

አይሁዶች። *ደግምም እስራኤል፣ ይሁዳ፣ የያዕቆብ ልጅ ተመልከቱ*

አይሁዶች (፩) ከያዕቆብ አስራ ሁለት ወንድ ልጆች መካከል አንዱ የይሁዳ ትውልድ፣ (፪) የጥንቱ የደቡብ የይሁዳ መንግስት ህዝቦች፣ ወይም (፫) የይሁዳነት ሀይማኖት፣ የህይወት አኗኗር፣ እና ባህል የሚከተሉ፣ ነገር ግን በተወለዱበት አይሁዳ ለመሆን ወይም ላለመሆን የሚችሉ ሊሆኑ ይችላሉ። የያዕቆብ ትውልዶችን በሙሉ ለመጠቆም ይሁዳ በሚባለው ቃል መጠቀም ባህል ሆኗል፣ ነገር ግን ይህ ስህተት ነው። ይህ ለይሁዳ መንግስት ወይም በተለይ ዛሬ የይሁዳ ጎሳዎችን እና ከእነርሱ ጋር የተገናኙትን ለመጠቆም የተወሰነ መሆን ይገባዋል።

በትረ መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም. . . ገዥ የሆነው እስኪመጣ ድረስ፣ ዘፍጥ. ፴፱፡፲።

የኢየሱስ ወንጌል አስቀድሞ ለአይሁዳዊ፣ ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነው፣ ሮሜ ፩፡፲፮።

ጌታ እግዚአብሔር ከአይሁዶች መካከል ነቢይን፣ እንዲሁም መሲሁን ያስነሳል፣ ፩ ኔፊ ፲፡፱። መፅሐፉ ከአይሁድ አፍ በወጣበት ጊዜ ነገሮች ግልፅና የጠሩ ነበሩ፣ ፩ ኔፊ ፲፱፡፳–፳፫። አይሁዶች በሀገር ሁሉ መካከል ይበተናሉ፣ ፪ ኔፊ ፳፭፡፲፮። አይሁዶች የጥንት የቃል ኪዳን ህዝቦቼ ናቸው፣ ፪ ኔፊ ፳፱፡፲። የተበተኑት አይሁዶች ደግሞ በክርስቶስ ማመን ይጀምራሉ፣ ፪ ኔፊ ፴፡፯። አይሁዶች የደህንነት መሰረት የሚያገኙበትን አለቱን አይቀበሉም፣ ያዕቆ. ፱፡፲፱–፲፯። አይሁዶች ኢየሱስ የጥንቱ ክርስቶስ እንደሆነ ሌላ ምስክር ይኖራቸዋል፣ ሞር. ፣፡፳–፳፭።

ሁለት ነቢያት ለአይሁዶች እንዲተነቢዩ በአይሁድ ሀግሮች ይነሳሉ፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፲፭። መጀመሪያ ወደ አህዛብ እና ከዚያም ወደ አይሁዶች፣ ሁሉንም ሀገሮች ይጥሯቸው፣ ት. እና ቃ. ፻፴፣፡፳። በዚያን ጊዜ ታላቅ ስቃይ በአይሁዶች ላይ ይደርሳል፣ ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፡፲፰።

አይነ አፋርነት። *መጠነኛነት ተመልከቱ*

አይን፣ አይኖች

በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ፣ አይን የእግዚአብሔርን ብርሀን ለመቀበል ሰው እንዳለው ችሎታ ምሳሌ በብዙ ጊዜ የሚጠቀሙበት ነው። በምሳሌም፣ የሰው አይን የመንፈሳዊ ጉዳይን እና የእግዚአብሔር ነገሮችን ማስተዋልን ያሳያል።

የእግዚአብሔር ትእዛዝ ብሩህ ነው፥ ዓይንንም ያበራል፣ መዝ. ፲፱፡፰። ሰነፎች ዓይን እያላችሁ አታዩም፣ ኤር. ፭፡፳፩ (ማር. ፰፡፲፰)።

የሰውነት መብራት ዓይን ናት፣ ማቴ. ፮፡፳፪ (ሉቃ. ፲፩፡፴፬፣ ፣ ኔፊ ፲፣፡፳፪፣ ት. እና ቃ. ፹፰፡፳፯)። የእናንተ ግን ዓይኖቻችሁ ስለሚያዩ ብፁዓን ናቸው፣ ማቴ. ፲፣፡፲፮። የማስተዋላችሁ አይኖች ብሩህ ይሆናሉ፣ ኤፌ. ፩፡፲፯–፲፰።

በራሳቸው ዐይን ብልህና አስተዋይ ለሆኑት ወዮላቸው፣ ፪ ኔፊ ፲፭፡፳፩ (ኢሳ. ፭፡፳፩)። የህዝቡም ዐይን እንዲከፈት፣ መፀለይ እናም መዖም ጀመሩ፣ ሞዛያ ፳፯፡፳፪። ሰይጣን አሳውሮአቸዋል፣ ፣ ኔፊ ፪፡፪። ለእግዚአብሔር ክብሩ በቀናነት ካላደረገ በስተቀር ማንም መፅሐፈ ሞርሞንን ለማምጣት ሀይል አይኖረውም፣ ሞር. ፰፡፲፭።

፲፪ በመንፈስ ሀይልም፣ አይኖቻችን ተከፈቱ እናም እውቀቶቻችንም ብሩህ ሆኑ፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፲፪። አይኖቻችሁን የሚያበራው ብርሀንም በእርሱ በኩል ነው፣ ት. እና ቃ. ፹፰፡፲፩። ለክብሬ ዐይናችሁ ቀና ብትሆን፣ ሰውነታችሁ ሁሉ ብሩህ ይሆናል፣ ት. እና ቃ. ፹፰፡፳፯።

አዲሲቱ ኢየሩሳሌም። *ደግምም ፅዮን ተመልከቱ*

ቅዱሳን የሚሰበሰቡበት እና ክርስቶስ በአንድ ሺህ አመት ዘመን እራሱ የሚነግስበት ቦታ። ፅዮን (አዲሲቱ ኢየሩሳሌም) በአሜሪካ ክፍል አህጉራት ውስጥ ትመሰረታለች፣ ምድርም ትታደሳለች እናም እንደ ገነት አይነት ክብር ትቀበላለች (እ.አ. ፩፡፲)። ይህም

በአንድ ሺህ ዘመን ጊዜ ከሰማይ የምትወርደውን ቅዱስ ከተማን ይጠቁማል።

ከጽዮን ሕግ ይወጣል፣ ሚክ. ፬፡፪።

የጌታ ከተማ ስም አዲሲቱን ኢየሩሳሌም ነው፣ ራዕ. ፲፡፲፪። ዮሐንስ ቅዱስ ከተማዋን፣ አዲሲቱን ኢየሩሳሌም አየ፣ ራዕ. ፳፩፡፩–፫።

ይህን ህዝብ በዚህች ምድር እመሰርታለሁ፤ እርሷም አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ትሆናለች፣ ፲ ኄፊ ፳፡፳፪። አዲሲቱ ኢየሩሳሌም በአሜሪካ ትመሰረ ታለች፣ ኤተር ፲፫፡፲–፲፯፣ ፲።

አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ከተማ ትዘጋጃለች፣ ት. እና ቃ. ፵፪፡፱፣ ፴፭፣ ፴፪–፴፱። ቅዱሳን ይሰ ብሰቡ እናም አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን ይመስርቱ፣ ት. እና ቃ. ፵፭፡፴፫–፴፭። አዲስቱ ኢየሩሳሌም በምዙሪ ተመሰረታለች፣ ት. እና ቃ. ፲፱፡፩–፫ (ት. እና ቃ. ፶፯፡፩–፲)። በጉ በፅዮን ተራራ ላይና በቅዱስ ከተማ፣ በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ላይ ይቆ ማል፣ ት. እና ቃ. ፲፴፫፡፶፯።

ድንኳኔም ፅዮን፣ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ተብላ ትጠራለች፣ ሙሴ ፯፡፴፪።

አዲስ እና የዘለአለም ቃል ኪዳን። *ደግምም ቃል ኪዳን ተመልከቱ*

የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ሙላት (ት. እና ቃ. ፴፯፡፪)። ከክህደት ጊዜ በኋላ እንደ አዲስ በሚ ገለጽበት ጊዜ ሁሉ አዲስ ነው። ይህም ዘለአለ ማዊ የሚሆነው የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ስለሆ ነና ሰዎች ይህን ለመቀበል ፈቃደኛ በሆኑበት በእ ያንዳንዱ የወንጌል ዘመን ይደሰቱበት የነበረ ስለ ሆነ ነው። አዲሱ እና የዘለአለም ቃል ኪዳን በኢ የሱስ ክርስቶስ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል እንደ ገና በምድር ላይ ለሰዎች ተገለጸ። ይህም በክህነት ስልጣን በኩል የሚከናወኑ ለሰው ደህንነት፣ ህያ ውነት፣ እና ዘለአለማዊ ህይወት ዝግጅት የሚያቀ ርቡ እንደ ጥምቀት እና የቤተመቅደስ ጋብቻ አይ ነት ቅዱስ ስነስርዓቶችን የያዘ ነው። ሰዎች ወንጌ ልን ሲቀበሉ እና የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ለማ ክበር ቃል ሲገቡ፣ እግዚአብሔር የአዲስ እና የዘ ለአለም ቃል ኪዳን በረከቶችን ለእነርሱ ለመስጠት ቃል ኪዳን ይገባል።

ቃል ኪዳኔንም በእኔና በአንተ መካከል አቆማ ለሁ፣ ዘፍጥ. ፲፯፡፯። ለእርሱ ክህነት ቃል ኪዳን ይሆንለታል፣ ዘኁል. ፳፭፡፲፫። ሰዎች ሥርዓቱ ንም ለውጠዋልና፥ የዘላለሙንም ቃል ኪዳን አፍ ርሰዋል፣ ኢሳ. ፳፬፡፭ (ት. እና ቃ. ፭፡፲፭)። የዘላ ለምን ቃል ኪዳን ከእናንተ ጋር አደርጋለሁ፣ ኢሳ. ፶፭፡፣ (ኤር. ፴፪፡፴)። የዘላለምም ቃል ኪዳን ይሆ ንላቸዋል፣ ሕዝ. ፴፯፡፳፯።

ጌታ አዲስ ቃል ኪዳን ሰራ፣ እናም አዲሱን አስረጅታል፣ ዕብ. ፰፡፲፣ ኢየሱስ የአዲስም ኪዳን መካከለኛ ነው፣ ዕብ. ፲፪፡፳፬ (ት. እና ቃ. ፳፯፡፳፱)።

ይህ አዲስ እና ዘለአላለማዊ ቃል ኪዳን ነው፣ ት. እና ቃ. ፳፪፡፩። ዘለአለማዊ ቃል ኪዳኔን ወደ አለም ላኩኝ፣ ት. እና ቃ. ፵፭፡፱ (ት. እና ቃ. ፵፱፡፱)። ጌታ የወንጌሌን ሙሉነት፣ የዘለአለም ቃል ኪዳኑን ላከ፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፪ (ት. እና ቃ. ፲፴፫፡፶፯)። ከፍተኛውን የሰለስቲያል ክብር ለማግ ኘት፣ ሰው ወደ አዲስ እና ዘለአለማዊ የጋብቻ ቃል ኪዳን መግባት አለበት፣ ት. እና ቃ. ፲፴፭፡፩–፪። አዲስ እና ዘለአለማዊ ቃል ኪዳን የተመሰረተው ለጌታ ክብር ሙላት ነው፣ ት. እና ቃ. ፲፴፪፡፯፣ ፲፴።

አዲስ ኪዳን። *ደግምም መፅሐፍ ቅዱስ፤ ቅዱሳት መጻህፍት ተመልከቱ*

ስለኢየሱስ ክርስቶስ፣ ስለሐዋሪያት፣ እና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች ህይወት እና አገልግ ሎት የሚገልጹ (በግሪክ ቋንቋ በመጀመሪያ የተ ጻፉ) የተነሳሱ ጽሁፎች። አዲስ ኪዳን በወንጌሎች፣ በሐዋርያት ስራ፣ በጳውሎስ መልእክቶች፣ አጠ ቃላይ መልእክቶች፣ እና በራዕይ መፅሐፍ የተከ ፋፈሉ ናቸው።

አራቱ ወንጌሎች፣ የማቴዎስ፣ የማርቆስ፣ የሉ ቃስ፣ እና የዮሐንስ መፅሐፎች የክርስቶስ ህይወት ታሪኮች ናቸው። የሐዋርያት ስራ የቤተክርስቲያኗን እና የሐዋሪያትን፣ በልዩም ከክርስቶስ ሞት በኋላ የጳውሎስን የሚስዮን ጉዞ ታሪክ ይመዘግባል። የጳ ውሎስ ደብዳቤዎች የቤተክርስቲያኗን መሪዎችና አባላት ያስተምራል። ሌሎቹ ደብዳቤዎች የተጻ ፉት በሌሎች ሐዋሪያት ነበር እናም የመጀመሪያ ቅዱሳንን ተጨማሪ ምክር የሚሰጥ ነበር። በሐዋሪ ያው ዮሐንስ የተጻፈው የዮሐንስ ራዕይ ስለመጨ ረሻ ቀናት ትንቢቶችን የያዘ ነው።

አዳም። *ደግምም ሔዋን፤ ሚካኤል፤ አዳም-አንዳይ-አማን፤ ዓድን፤ የመላእክት አለቃ፤ የአዳም እና የሔዋን ውድቀት ተመልከቱ*

በምድር ላይ የተፈጠረ የመጀመሪያ ሰው።

አዳም የምድር ሰው ዘር አባት እና የአባቶች አለቃ ነው። በዓድን ገነት ውስጥ የተላለፈው (ዘፍጥ. ፫፤ ት. እና ቃ. ፳፪፡፵–፵፪፤ ሙሴ ፩) “እንዲወድቅ” እና ሟች ሆነ፣ ይህም የሰው ዘር በዚህ ምድር ላይ እድገት እንዲኖራቸው አስፈላጊ የሆነ ደረጃ ነበር (፪ ኔፊ ፪፡፲፩–፳፭፤ አልማ ፲፪፡፳፭–፳፯)። ስለዚህ አዳም እና ሔዋን የዘለአለማዊ እድገት እንዲኖረን ስላስቻሉን ለስራ ክፍላቸው መከበር ይገባቸዋል። አዳም በዘመናት የሸመገለውም እና ሚካኤል ተብሎ የሚታወቀው ነው (ዳን. ፯፤ ት. እና ቃ. ፳፯፡፲፤ ፲፯፡፹–፹፩፤ ፲፲፯፤ ፲፴፯፡፴፯)። እርሱም የመላ

እክት አለቃ ነው (ት. እና ቃ. ደ፯፡፹፱) እና እንደ ሰው ቤተሰብ የአባቶች አለቃ፣ ለኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት ዝግጅት እንደገና ወደ ምድር ይመ ጣል (ት. እና ቃ. ፲፲፯)።

እግዚአብሔር ሰውን በመልኩ ፈጠረ፣ ዘፍጥ. ፩፡፳፯–፳፰ (ሙሴ ፪፡፳፯–፳፰፣ አብር. ፬፡፳፯–፳፰)። እግዚአብሔር ሰውን በሁሉም ነገሮች ላይ ገዝነት ሰጠው እና እንዲባዛ እና ምድርን እንዲ ሞላ አዘዘው፣ ዘፍጥ. ፩፡፳፰–፴፩ (ሙሴ ፪፡፳፰–፴፩፣ አብር. ፬፡፳፰–፴፩)። እግዚአብሔር አዳም እና ሔዋንን በዔድን ገነት ውስጥ አኖራቸው እና መልካምንና ክፉን የሚያስታውቀውን ዛፍ እንዳ ይበሉም ከለከላቸው፣ ዘፍጥ. ፪፡፮–፱፣ ፲፭–፲፯ (ሙሴ ፫፡፮–፱፣ ፲፭–፲፯፣ አብር. ፭፡፮–፲፣)። አዳም ሕያው ነፍስ ላለው ሁሉ ስም አወጣላቸው፣ ዘፍጥ. ፪፡፲፱–፳ (ሙሴ ፫፡፲፱–፳፡ አብር. ፭፡፳–፳፩)። አዳም እና ሔዋን በእግዚአብሔር ተጋቡ፣ ዘፍጥ. ፪፡፲፳–፳፫ (ሙሴ ፫፡፲፳–፳፫፣ አብር. ፭፡፲፱–፳፩)። አዳም እና ሔዋን በሰይጣን ተፈ ተኑ፣ የተከለከለውን ፍሬ በሉ፣ እና ከዔድን ገነ ትም ወጡ፣ ዘፍጥ. ፣ (ሙሴ ፱)። አዳም ሲሙት እድሜው ፱፻፴ ነበር፣ ዘፍጥ. ፭፡፭ (ሙሴ ፮፡፲፪)።

አዳም የመጀመሪያ ሰው ነበር፣ ት. እና ቃ. ፹፱፡፲፮። ከመሞቱ በፊት አዳም ጻድቅ ዘሮቹን በአ ዳም-ኦንዳይ-አማን ውስጥ ሰበሰበ እና ባረካቸው፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፹፫–፹፯።

አዳን መስዋዕት አቀረበ፣ ሙሴ ፭፡፱–፳። አዳም ተጠመቀ፣ መንፈስ ቅዱስን ተቀበለ፣ እና ለክህነት ስልጣን ተሾመ፣ ሙሴ ፮፡፶–፳፫።

አዳም-ኦንዳይ-አማን። *ደግምም አዳም ተመልከቱ*

ከመሞቱ ሶስት አመት በፊት አዳም ዘሮቹን የባ ረከበት (ት. እና ቃ. ፲፯፡፹፫–፹፯) እና ከዳግም ምፃት በፊት እንደገና የሚመጣበት ቦታ (ት. እና ቃ. ፲፲፯)።

አዳኝ። *ደግምም ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልከቱ*

የሚያድን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ በኃጢያት ክፍያ በኩል፣ ለሰው ዘር ቤዛነት እና ደህንነትን አቀረበ። “አዳኝ” የኢየሱስ ክርስቶስ ስም እና ርዕስ ነው።

እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው፣ መዝ. ፳፯፡፩ (ዘፀአ. ፲፭፡፩–፪፣ ፪ ሳሙ. ፳፪፡፪–፫)። እኔ፡ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፡ ከእኔ ሌላም የሚያ ድን የለም፣ ኢሳ. ፵፫፡፣፩ (ት. እና ቃ. ፷፯፡፩)።

እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ፣ ማቴ. ፩፡፳፩ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋል፣ ሉቃ. ፪፡፲፩ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና፣ ዮሐ. ፫፡፲፯–፲፯ ከክርስቶስ በስተ ቀር ሰው የሚዳንበት ምንም ሌላ ስም የለም፣ የሐዋ. ፬፡፲–፲፪ (፪ ኔፊ ፳፭፡፳፣ ሞዛያ ፫፡፲፣ ፭፡፳፣ ት. እና ቃ. ፲፳፡፳፫፣ ሙሴ ፮፡፶፪)። ከሰማይ መድ ኃኒትን፣ ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለን፣ ፊልጵ. ፫፡፳። አባትም ልጁን የዓለም መድኃኒት ሊሆን ላከው፣ ፩ ዮሐ. ፬፡፲፬።

ጌታ እግዚአብሔር መሲሁን፣ የዓለምን መድ ኃኒት ያስነሳል፣ ፩ ኔፊ ፲፡፬። የእግዚአብሔርም በግ የአለም አዳኝ እንደሆነ፣ ፩ ኔፊ ፲፫፡፴። የአ ዳኞችን እውቀት በሁሉም ሀገር፣ ነገድ፣ ቋንቋ እና ህዝብ መካከል ይሰራጫል፣ ሞዛያ ፫፡፳። ደህን ነት እንዲመጣ ክርስቶስ መሞት ይገባዋል፣ ሔሌ. ፲፬፡፲፭–፲፯።

በአዳኞችን በኩል የሚገኘው ጽድቅነትና ቅድስና ትክክል እና እውነተኛ ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፳፡፴–፴፩። እኔ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ የአለም አዳኝ ነኝ፣ ት. እና ቃ. ፴፫፡፴፱።

አንድያ ልጁም አዳኝ ነው፣ ሙሴ ፩፡፮። በወ ልድ ያመኑትና ለኃጥያታቸው ንስሀ የገቡት ሁሉ ይድናሉ፣ ሙሴ ፭፡፲፭።

አድናቆት። *አመስጋኝ፣ ምስጋናን፣ ምስጋና መስጠት፣ ክብር ተመልከቱ*

አገልጋይ መላእክት። *መላእክት ተመልከት*

አገልግሎት። *ደግምም በጎ ድርጊት፣ ክህነት፣ ፍቅር ተመልከቱ*

የጌታን ስራ በምድር ላይ ማከናወን። ለእግዚ አብሔር እና ለሌሎች ጥቅም የተሰጠ እንክብካቤ ወይም የተፈጸመ ስራ። ሌሎችን ስናገለግል፣ እግ ዚአብሔርንም ማገልገላችን ነን። የጌታ የተመረጡ አገልጋዮች በስራው ውስጥ ለማገልገል በእግዚአ ብሔር መጠራት አለባቸው። እውነተኛ አገልጋ ዮች የጌታን ፍላጎት ሲያከናውኑ፣ በዋና ሀላፊነታ ቸው ጌታን ይወክላሉ እናም እንደ እርሱ ወኪሎችም ይሰራሉ (ት. እና ቃ. ፳፬፡፳፩)፣ በዚህም ለሰው ደህ ናነት አስፈላጊ ስራዎችን ያከናውናሉ። ጌታ ሐዋሪ ያት፣ ነቢያት፣ ወንጌልን ሰባኪዎች፣ ሊቀ ካህናት፣ ሰባዎች፣ ሽማግሌዎች፣ ኤጲስ ቆጶሳት፣ ካህናት፣ አስተማሪዎች፣ ዲያቆኖች፣ ረዳቶች፣ እና አስተ ዳዳሪዎች ቅዱሳንን ፍጹም ለማድረግ እና ለአገል ግሎት ስራ ሰጥቷል (፩ ቆሮ. ፲፪፡፲፪–፳፰፣ ኤፌ. ፬፡፲፩–፲፮፣ ት. እና ቃ. ፳፡ ፲፯)።

በእግዚአብሔር ስም ያገለግል ዘንድ አምላክህ መረጠው፣ ዘዳግ. ፲፰፡፭። የምታገለግሉትን ዛሬ ምረጡ፣ ኢያ. ፳፬፡፲፭። ሰዎቹም የአምላካችን አገልጋዮች ብለው ይጠሩአችኋል፣ ኢሳ. ፰፩፡፮።

የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም፣ ማቴ. ፳፡፳፭–፳፰። ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ለአንዱ

ስላላደረጋችሁት ለእኔ ደግሞ አላደረጋችሁትም ብሎ ይመልስላቸዋል፣ **ማቴ.** ፳፭፡፡፴–፴፭። ለአ ንተም በምታይበት ነገር አገልጋይና ምስክር ትሆን ዘንድ ልሾምህ ታይቼልሃለሁ፣ **የሐዋ.** ፳፮፡፲፮–፲፰። ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያ ሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ፣ **ሮሜ** ፲፪፡፩። በፍቅር እርስ በርሳችሁ እንደ ባሪ ያዎች ሁኑ፣ **ገላ.** ፭፡፲፫። እግዚአብሔር፡ ቅዱሳ ንን ስላገለገላችሁ እስከ አሁንም ስለምታገለግሉአ ቸው፡ ያደረጋችሁትን ሥራ ለስሙም ያሳያችሁ ትን ፍቅር ይረሳ ዘንድ ዓመፀኛ አይደለምና፣ **ዕብ.** ፮፡፲። ማንም ሰው የሚያገለግልም ቢሆን፡ እግዚ አብሔር በሚሰጠኝ ኃይል ነው ብሎ ያገልግል፣ **፩ ጴጥ.** ፬፡፣–፲፩።

ቀናትህን አምላክህን በማገልገል ታሳልፋለህ፣ **ፍ ኔሬ** ፪፡፫። እናንተ ሰዎችን በምታገለግሉበት ጊዜ እግዚአብሔርን ብቻ እያገለገላችሁ ናችሁ፣ **ሞዛያ** ፪፡፲፯። አንዳቸው ሌላኛውን አገለገሉ፣ እናም አስ ተማሩ፣ **ፍ ኔሬ** ፳፮፡፲ፀ። የቃል ኪዳን ምድርን የሚ ይዙ እግዚአብሔርን ማገልገል ወይም ተጠርገው መውጣት አለባቸው፣ **ኤተር** ፪፡፯–፲፪።

እናንተ በእግዚአብሔር አገልግሎት ውስጥ መሳ ተፍ የጀመራችሁ፣ በፍጹም ልባችሁ እንደምታገ ለግሉት አረጋግጡ፣ **ት. እና ቃ.** ፬፡፪። ጌታ እግ ዚአብሔርን እንዲወዱና እንዲያገለግሉ ትእዛዞች ሰጣቸው፣ **ት. እና ቃ.** ፳፡፣–፲፱። በኢየሱስ ክር ስቶስ ስም አገልግለው፣ **ት. እና ቃ.** ፶፱፡፭። እኔ ጌታ ለየሚያገለግሉኝንም ለማክበር እደሰታለሁ፣ **ት. እና ቃ.** ፹፯፡፭። ወንጌል ሰባኪዎችን መሾም የአስራ ሁለቱ ሀላፊነት ነው፣ **ት. እና ቃ.** ፲፯፡፴፱–፴፯። ሊቀ ካህን በስጋዊ ነገሮች ለማስተዳደር መለ የት ይቻላል፣ **ት. እና ቃ.** ፲፯፡፹፭–፹፪። እነዚህ ሰባዎች ተጓዥ አገልጋዮች ናቸው፣ **ት. እና ቃ.** ፲፯፡፣፲–፣፯። ሽማግሌዎች የተሾሙት የቤተክ ርስቲያኗ የማይጓዙ አገልጋዮች እንዲሆኑ ነው፣ **ት. እና ቃ.** ፲፳፬፡፲፴፯።

እግዚአብሔርን አምልክ፣ እርሱን ብቻም አገል ግል፣ **ሙሴ** ፭፡፣፲፭።

አጋር። *ደግሞም አብርሐም፤ እስማኤል፣ የአብርሐም ልጅ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የሳራ ግብጻዊ ገረድ። የአብርሐም ባለቤት እና የእስማኤል እናት ሆነች (ዘፍጥ. ፣፯፤ ፳፭፡፣፲፪፤ ት. እና ቃ. ፲፴፪፡፴፣፡ ፳፭)። ጌታ ከልጇ ታላቅ ህዝብ እንደሚመጡ ለአ ጋር ቃል ገባላት (ዘፍጥ. ፳፩፡፱–፳፩)።

አጋንንት። *ዲያብሎስ ተመልከቱ*

አግሪጳ። *ደግሞም ጳውሎስ ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ የመጀመሪያው ሔሮድስ አግሪጳ ወንድ ልጅ እና የበርኒቄ እና የድሩሲላ ወንድም። በሊባኖስ ውስጥ በሚገኘው፣ የቻልስስ ንጉስ። ሐዋሪያው ጳውሎስን ሰማ እና ክርስትያን ወደመሆን ለማመን ቀርቦ ነበር (የሐዋ. ፳፭–፳፮፤ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፳፬)።

አጠቃላይ ባለስልጣኖች። *ሐዋሪያ፤ ሰባ፤ ቀዳሚ አመራር፤ የኤጲስ ቆጶስ አመራር ተመልከቱ*

አጥቢያ ኮከብ። *ደግሞም ሲያል፤ አፍራሽ፤ የክርስቶስ ተቃዋሚ፤ የጥፋት ልጆች፤ ዲያብሎስ ተመልከቱ*

ስሙ "የሚበራው" ወይም "ብርሀን ያዝው" ማለት ነው። እርሱ የንጋት ልጅ ተብሎ ይታወ ቃል። አጥቢያ ኮከብ የሰማይ አባት የመንፈስ ልጅ ነበር እናም በቅድመ ምድር ህይወት አመፅን መራ። የአጥቢያ ኮከብ ስም በመፅሐፍ ቅዱስ የሚገኘው አንድ ጊዜ ብቻ ነው (ኢሳ. ፲፬፡፲፪)። የኋለኛው ቀን ራዕይ ስለአጥቢያ ኮከብ መውደቅ ተጨማሪ ዝርዝር ይሰጣል (ት. እና ቃ. ፷፯፡፳፭–፳፱)።

አጥቢያ ኮከብ በቅድመ ምድር ህይወት ወደቀ፣ **ኢሳ.** ፲፬፡፣፲፪ (ሉቃ. ፣፡፣፰፣ ፪ ኔሬ ፳፬፡፣፲፪)።

ከወደቀ በኋላ ሰይጣን እና ዲያብሎስ ሆነ፣ **ት. እና ቃ.** ፷፯፡፳፭–፳፱ (ሙሴ ፬፡፩–፬)።

አጥፊ። *አፍራሽ ተመልከቱ*

አፅናኝ። *ደግሞም መንፈስ ቅዱስ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልከቱ*

ቅዱሣት መጻህፍት ስለሁለት አፅናኞች ይናገ ራሉ። የመጀመሪያው መንፈስ ቅዱስ ነው (ዮሐ. ፲፬፡፳፭–፳፯፤ ሞሮኒ ፯፡፳፯፤ ት. እና ቃ. ፳፭፡፱፤ ፵፪፡፲፣፤ ፣፡፣፩)። ሁለተኛው አፅናኝ ጌታ ኢየ ሱስ ክርስቶስ ነው (ዮሐ. ፲፬፡፲፣፡ ፳፭፤ ፳፫)። አንድ ሰው ሁለተኛውን አፅናኝ ሲያገኝ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ከጊዜ ወደጊዜ ለእርሱ ይታየዋል፣ አብን ይገልፅለታል፣ እናም ፊት ለፊትም ያስተምረዋል (ት. እና ቃ. ፲፱፡፣–፣)።

አፍራሽ። *ደግሞም ዲያብሎስ ተመልከቱ*

ሰይጣን አጥፊው ነው።

እግዚአብሔር አጥፊው ወደ ቤታችሁ እንዲገባ አይተውም፣ **ዘፀአ.** ፲፪፡፳፫።

አጥፊው በውሀው ላይ ይንሳፈፋል፣ **ት. እና ቃ.** ፳፭፡፲፱። ጠባቂው የወይን ስፍራዬን ከአጥፊው ሊያድኑት ይችሉ ነበር፣ **ት. እና ቃ.** ፲፭፡፶፭–፶፩።

አፖክሪፋ። *ደግሞም መፅሐፍ ቅዱስ፤ ቅዱሳት መጻህፍት ተመልከቱ*

በእብራውያን መፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያልተጨ

መሩት ነገር ግን በአንዳንድ የክርስትያን ቤተክርስ ትያናት ውስጥ የሚገኙት የአይሁድ ህዝቦች ቅዱሣት መጻህፍት። እነዚህ መጽሀፎች በብዙ ሁኔታዎች ብሉይ እና አዲስ ኪዳኖችን ለማያያዝ ጠቃሚ ናቸው እና በቤተክርስትያኗ ውስጥ እንደ ጠቃሚ ምንባብ አስተያየት ይሰጣቸዋል።

አፖክርፋ በብዙ ጊዜ በትክክል የተተረጎሙ ናቸው ነገር ግን ትክክል ያልሆነ ጣልቃዎች ገብ ተውባቸዋል፣ ት. እና ቃ. ፯፩፡፩–፫። አፖክርፋ በመንፈስ የተብራሩትን ለመጠቀም ይችላል፣ ት. እና ቃ. ፯፩፡፱–፲፮።

ኡሪም እና ቱሚም። *ደግሞም ባለራዕይ፤ የደረት ኪስ ተመልከቱ*

ሰውን ራዕይን ለማግኘት እና በቋንቋዎች ለመተ ርጎም በእግዚአብሔር የተዘጋጀ መሳሪያ። በእብራ ውያን ቋንቋ ቃላቶቹ “ብርሀኖች እና ፍጹምነቶች” ማለት ነው። ኡሪም እና ቱሚም በብር ቀሰት ላይ የተቀመጥ ሁለት ድንጋዮች ያሉበት እናም አንዳንድ ጊዜም ከጥሩር ጋር ይጠቀሙበት ነበር (ት. እና ቃ. ፲፯፡፩፤ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፴፭፣ ፴፪፣ ፴፪)። ይህች ምድር በተቀደሰችበት እና በአለሟችነት ሁኔታዋ ታላቅ ኡሪም እና ቱሚም ትሆናለች (ት. እና ቃ. ፲፴፡፲–፱)።

በፍርዱ በደረት ኪስም ውስጥ ኡሪምንና ቱሚ ምን ታደርጋለህ፣ **ዘፀአ.** ፳፰፡፴፡፴።

ድል ለነሣው ነጭ ድንጋይንም እሰጠዋለሁ፣ ራዕ. ፪፡፣ ፲፯።

እርሱ የሚመለከትበት ለመተርጎም የሚችል በት አለው፣ **ሞዛያ** ፰፡፲፫። እነዚህን ሁለት ድን ጋዮች እሰጥሃለሁ፣ **ኤተር** ፫፡፳፫–፳፭፣ ፳፡፳ (ኤተር ፭፡፩)።

ጆሴፍ ስሚዝ በኡሪም እና ቱሚም በኩል ራዕ ዮችን ተቀበለ፣ ት. እና ቃ. ክፍሎች ፯፣ ፲፩፣ ፲፬–፲፯ መግቢያዎች። በኡሪም እና ቱሚም አማካኝነት እንድትተረጉም ኃይል ተሰጥተውሀል፣ ት. እና ቃ. ፲፡፩። ሶስቱ ምስክሮች ለያሬድ ወንድም የተሰጡ ትን ኡሪም እና ቱሚም ይመለከታሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፩። እግዚአብሔር የሚኖርበት ቦታምታላቅ ኡሪም እና ቱሚም ነው። ነጩ ድንጋይ ለሚቀበ ሉት ግለሰቦች ሁሉ ኡሪም እና ቱሚም ይሆናሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፴፡፮–፲፩።

እኔ፣ አብርሐም፣ ኡሪም እና ቱሚም ነበረኝ፣ **አብር.** ፫፡፩፣ ፱።

ኢሊያ። *ደግሞም ኤልያስ ተመልከቱ*

ኤልያስ የሚባለው ስም ወይም ርዕስ በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ የተለያዩ ጥቅም ነበራቸው።

ቀደምትነት ያለው፣ ኤልያስ ቀደምትነት ላለው የተሰጠ ርዕስም ነው። ለምሳሌ፣ መጥምቁ ዮሐንስ ኤልያስ የነበረው ለኢየሱስ መንገድን እንዲያዘጋጅ ስለተላከ ነው (ማቴ. ፲፯፡፲፪–፲፫)።

ደግሞ የሚልክ፣ የኤልያስ ርዕስ እንደ ባለራዕዩ ዮሐንስ አይነት ልዩ ሚስዮንን ለሚያሟሉት ተሰ ጥቷል (ት. እና ቃ. ፳፯፡፲፱) (ሉቃ. ፩፡፲፩–፳፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፮–፯፣ ፲፲፡፲፪)።

በአብርሐም ዘመን የነበረ ሰው፣ በአብርሐም ቀናት ይኖር የነበረ ኢሳይያስ ወይም ኤልያስ ተብሎ የተጠራ ነቢይ (ት. እና ቃ. ፹፬፡፲፩–፲፫፣ ፲፲፡፲፪)።

ኢሳይያስ

ከ፯፻፵–፯፻፩ ም.ዓ. ድረስ የተነበየ የብሉይ ኪዳን ነቢይ። እንደ ንጉስ ሕዝቅያስ ዋና አማካሪ፣ ኢሳይ ያስ ታላቅ የሀይማኖትና የፖለቲካ ተፅዕኖ ነበረው። ኢሳይያስ በአብርሐም ቀናት ይኖር የነበረ ነቢይ ነበር (ት. እና ቃ. ፳፯፡፣ ፹፬፡፲፫)።

አሪት ዘፀአት። *ደግምም አምስቱ መጻህፍት ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ እስራኤላዊያን ከግብፅ የወ ጡበትን የሚገልፅ በሙሴ የተጻፈ መፅሐፍ። በአሪት ዘጸዓት ውስጥ በመጀመሪያ የተጻፉት የእስራኤል ታሪክ በሶስት ክፍሎች ለመከፋፈል ይችላሉ፥ (፩) የህዝቦቹ ለግብፅ ባሪያነት፣ (፪) በሙሴ አመራር ስር ከግብፅ የወጡበት፣ እና (፫) በሀይማኖት ህይወታ

ቸው እና በፖለቲካ ህይወታቸው እግዚአብሔርን ለማገልገል ስለወሰኑበት።

የመጀመሪያው ክፍል፣ ዘጸአት ፩፡፩–፲፭፡፳፭፣ እስራኤል በግብፅ መጨቆንን፤ የሙሴ የመጀመሪያ ታሪክ እና ጥሪ፤ ተነቅለው መሄዳቸው እና የፋሲካ መጀመር፤ እናም ወደ ቀይ ባህር ጉዞአቸው፣ የፈርዖን ሰራዊት ጥፋት፣ እና የሙሴ የድል መዝሙር።

ሁለተኛው ክፍል፣ ምጽአት ፲፭፡፳፪–፲፰፡፲፯፣ ስለእስራኤል ቤዛነት እና ከቀይ ባህር ወደ ሲና በተጓዙበት የደረሱ ነገሮች፤ የማራ ውሀዎች መራራ ነት፣ ድርጭቶች እና መና መሰጠታቸው፣ የሰም በት መከበር፣ በራፊዲም የተሰጠው የተአምራት የውሀ ስጦታ፣ እና ከአማሌቂውያን ጋር የተዋጉ በትን፤ ዮትር ወደሰፈሩበት መሄዱ እና ስለህዝባዊ መንግስት ስለነበረው ምክር ይናገራሉ።

ሶስተኛው ክፍል፣ ምዕራፍ ፲፱–፳፣ እስራኤል በሲና በነበራቸው የክብር ድርጊቶች ለእግዚአብ ሔር አገልግሎት ስለመቀደሳቸው ይናገራሉ። ጌታ ህዝቡን እንደ ካህናትና ቅዱስ ሀገሮች መንግስት ከፋፈላቸው፤ አስሩን ቃላት ሰጣቸው፤ እናም ስለ ታቦት፣ ስለእቃዎቹ፣ እና በእዚያም ውስጥ ስለ ማምለክ መመሪያ ሰጠ። ከእዚያም ህዝቦቹ የወርቅ ጥጃዎች በማምለክ ኃጢያት የሰሩበት ታሪክ ይቀ ጥላል፣ እናም በመጨረሻም የታቦት መሰራት እና ለአገልግሎቱ ዝግጅት ታሪክ አለ።

ኦሪት ዘፍጥረት። *ደግሞም አምስቱ መጻህፍት ተመልከቱ*

ኦሪት ዘፍጥረት የብሉይ ኪዳን የመጀመሪያ መፅ ሐፍ ነው እናም በነቢዩ ሙሴ የተጻፈ ነበር። ስለ ምድር መፈጠር፣ እንስሳትና ሰው በምድር ላይ መደረግ፣ የአዳምና የሔዋን ውድቀት፣ ለአዳም ስለተገለጸው የጎሳዎችና የዘሮች መጀመሪያ፣ የተ ለያዩ ቋንቋዎች በባቢሎን የተጀመሩበት፣ እናም ወደ እስራኤል ቤት መመስረት የመራው የአብር ሐም ቤተሰብ መጀመሪያ አይነት ብዙ የመጀመሪ ያዎች ታሪክ ይሰጣል። የጀሴፍ የእስራኤል አዳኝ ሀላፊነት በኦሪት ዘፍጥረት ውስጥ አፅንኦት ተሰ ጥቶታል።

የኋለኛው ቀን ራዕይ የኦሪት ዘፍጥረት ታሪኮችን ያረጋግጣል እናም ይገልጻል (፩ ኔፊ ፭፣ ኤተር ፩፣ ሙሴ ፩–፰፣ አብር. ፩–፭)።

በኦሪት ዘፍጠርት ውስጥ፣ ምዕራፍ ፩–፬ የአለም መፈጠርን እና የአዳም ቤተሰብ እድገት ታሪክን ይነ ግራሉ። ምዕራፍ ፭–፲ የኖህን ታሪክ ይመዘግባሉ። ምዕራፍ ፲፩–፳ እስከ ይስሐቅ ድረስ ስለ አብርሐ ምና ቤተሰቡ ይነግራሉ። ምዕራፍ ፳፩–፴፭ የይስሐ ቅን ቤተሰብ ይከተላሉ። ምዕራፍ ፴፮ ስለ ዔሳውና ቤተሰቡ ይናገራል ምዕራፍ ፴፯–፶ ስለ ያዕቆብ ቤተ ሰብና ወደ ግብፅ ስለተሸጠው ዮሴፍ እና የእስራኤል ቤትን ለማዳን ስላለው ሀላፊነት ታሪክ ይናገራሉ።

ከሞት መነሳት። ትንሳኤ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ *ተመልከቱ*

ከነዓናውያኑ ስምዖን

በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ ከኢየሱስ ክርስቶስ የመ ጀመሪያ ሐዋሪያት አንዱ (ማቴ. ፲፡፪–፬)።

ከነዓን፣ ከነዓናውያን

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የካም አራተኛ ልጅ (ዘፍጥ. ፱፡፳፪፤ ፲፡፭፣ ፮) እና የኖኅ የልጅ ልጅ። *ከነዓናውያን* ከነዓን በመጀመሪያ ከኖረበት ምድር የመጣ ሰው እና የእርሱ ትውልዶች የሚጠሩበት ነው። *ከነዓናውያንም* በፍልስጥኤም በሜዲትሬን ያን ባህር ዳር አካባቢ ቆላ ውስጥ ለሚኖሩት ህዝ ቦች የተሰጠ ስም ነው። ከዮርዳኖስ በስተምዕራብ ባለ ሀገር፣ ግሪኮች ፊኖሺያን ብለው የሚጠሩአቸ ውን እስራኤላውያን ያልሆኑ ነዋሪዎችን አንዳንዴ ለመግለፅ የሚጠቀሙበት ስም ነበር።

ከንቱ፣ ከንቱነት። *ደግሞም አለማዊነት፤ ኩራት ተመልከቱ*

ውስልት ወይም ውሸት፤ ኩራት ወይም ትዕቢት። *ከንቱ* እና *ከንቱነት* ደግሞም ባዶ ወይም ምንም ዋጋ የሌለው ማለት ሊሆንም ይችላል።

ነፍሱን ለከንቱ ያላነሣ በጌታ ቅዱስ ቦታ ላይ ይቆ ማል፣ **መዝ.** ፳፬፡፫–፬።

ስትጸልዩ በከንቱ አትድገሙ፣ **ማቴ.** ፮፡፯።

ከንቱ ሀሳብ እና ኩራት ትልቅ አስፈሪ ገደል ነው፣ **ፊ ኔፊ** ፲፪፡፲፰። ልባችሁን በከንቱ ምድራዊ ነገሮች እንዲሁም በሀብት ላይ ማድረጋችሁን አሁንም ትቀ ጥላላችሁን፣ **አልማ** ፭፡፶፫። የዚህን ዓለም ከንቱ ነገሮች አትፈልግ፤ ከአንተም ጋር ይዘሀቸው ለመ ሄድ አትችልም፣ **አልማ** ፴፬፡፲፭።

ከንቱነት እና ያለማመን ቤተክርስቲያኗን ሁሉ በፍርድ ላይ አድርገዋታል፣ **ት. እና ቃ.** ፹፬፡፹–፹፭። ኩራታችንን ከንቱ ፍላጎታችንን ለማርካት ስን ሞክር፣ ሰማያት እራሳቸውን ይለያሉ፣ **ት. እና ቃ.** ፲፳፭፡፴፯።

ከአንድ ሚስት በላይ ማግባት። *ጋብቻ፣ መጋባት—ከአንድ ሚስት በላይ ማግባት ተመልከቱ*

ከአንድ ሚስት በላይ የማግባት ባህል። *ጋብቻ፣ መጋባት—ከአንድ ሚስት በላይ ማግባት ተመልከቱ*

ከፍተኛ ሸንጎ

የአስራ ሁለት ሊቀ ካህናት ሸንጎ።

በቤተክርስቲያኗ ዳግም መመለስ መጀመሪያ ቀኖች፣ *ከፍተኛ ሸንጎ* ሁለት የተለያዩ የአመራር ክፍሎችን የሚጠቁም ነበር፡ (፩) የቤተክርስቲያኗ

አስራ ሐለት ሐዋሪያት ቡድን (ት. እና ቃ. ፻፯፥፴፫፤ ፴፰) እና በእያንዳንዱ ካስማዎች ውስጥ የሚያገለግሉ ከፍተኛ ሸንጎዎች (ት. እና ቃ. ፻፪፤ ፻፯፥፴፯)።

ከፍተኛነት። *ደግሞም* ሰው፣ ሰዎች—የሰው እንደ እግዚአብሔር አይነት ለመሆን ያለው ችሎታ፤ አክሊል፤ የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ፤ የሰለስቲያል ክብር፤ የዘለዓለም ህይወት *ተመልከቱ*

በሰለስቲያል መንግስት ውስጥ ታላቁ የደስታና የክብር ሁኔታ

ከፊትህ ጋር ደስታ፣ **መዝ.** ፲፮፥፲፩።

እነርሱ አማልክቶች፣ እንዲሁም የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው—ስለዚህ፣ ሁሉም ነገሮች የእነርሱ ናቸው፣ **ት. እና ቃ.** ፸፮፥፶፭–፶፱። ቅዱሳንም ውርሳቸውን ይቀበላሉ እና ከእርሱም ጋር እኩል ይደረጋሉ፣ **ት. እና ቃ.** ፹፰፥፻፯። እነዚህ መላእክቶች በህጎቼ አልኖሩም፤ ስለዚህ፣ ተለያይተው እና በብቸኝነት፣ ያለዘለአለማዊነት ይቆያሉ፣ **ት. እና ቃ.** ፻፴፪፥፲፯። ወንዶች እና ሴቶች ዘለአለማዊነትን ለማግኘት በእግዚአብሔር ህግ መሰረት መጋባት አለባቸው፣ **ት. እና ቃ.** ፻፴፪፥፲፱–፳። ወደ ዘለአለማዊነት መቀጠል የሚወስደው ደጅ የጠበበ፣ መንገዱም የቀጠነ ነው፣ **ት. እና ቃ.** ፻፴፪፥፳፪–፳፫። አብርሐም ይስህቅ፣ እና ያዕቆብ ወደ ዘለአለማዊነታቸው ገብተዋል፣ **ት. እና ቃ.** ፻፴፪፥፳፱፣ ፴፯። ዘለአለማዊነትህን አትምብሀለሁ፣ **ት. እና ቃ.** ፻፴፪፥፵፱።

ከፍተኛው ክህነት። የመልከ ጼዴቅ ክህነት *ተመልከቱ*

ኩራት። *ደግሞም* ሀብቶች፤ ትሁት፣ ትሕትና፤ አለማዊነት፤ ከንቱ፣ ከንቱነት፤ ገንዘብ *ተመልከቱ*

ትሕትና ወይም የመማር ችሎታ የሌለው። ትዕቢት ሰዎችን እርስ በራስ እና ከእግዚአብሔር ጋር የተቃረኑ እንዲሆኑ ያደርጋል። ትዕቢተኛ ሰው በአካባቢው ከሚገኙት እራሱን ከፍ ያደርጋል እናም የእግዚአብሔርን ፍላጎት ሳይሆን የእራሱን ፍላጎት ይከተላል። ጉረኛነት፣ ቅናት፣ ልበ ደንዳናነት፣ እና ኩራተኝነት የትዕቢተኛ ሰው ጸባይ ናቸው።

እግዚአብሔርን እንዳትረሳ ተጠንቀቅ፣ ልብህ እንዳይኳደድ፣ **ዘዳግ.** ፰፥፲፩–፲፬። ትዕቢትንና እብሪትን እጠላለሁ፣ **ምሳ.** ፰፥፲፫ (ምሳ. ፮፥፲፮–፲፯)። ትዕቢት ጥፋትን ይቀድማል፣ **ምሳ.** ፲፮፥፲፰። የእግዚአብሔር ቀን በትዕቢተኛው ላይ ይሆናል፣ **ኢሳ.** ፪፥፲፩–፲፪ (፪ ኔፊ ፲፪፥፲፩–፲፪)። የልብህ ትዕቢት አታልሎሃል፣ **አብድ.** ፩፥፫። ትዕቢተኞች ሁሉ ገለባ ይሆናሉ፣ **ሚል.** ፬፥፩ (፩ ኔፊ ፳፪፥፲፭፤ ፫ ኔፊ ፳፭፥፩፤ ት. እና ቃ. ፳፱፥፱)።

ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳል፣ **ማቴ.** ፳፫፥፲፪ (ት. እና ቃ. ፻፩፥፵፪)። እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፣ **፩ ጴጥ.** ፭፥፭።

ትልቁና ሰፊው ህንፃ የዓለም ኩራት ነው፣ **፩ ኔፊ** ፲፩፥፴፮ (፩ ኔፊ ፲፪፥፲፰)። በተማሩ ጊዜ ራሳቸውን እንደብልህ ይቆጥራሉ፣ **፪ ኔፊ** ፱፥፳፰–፳፱። በልባችሁ ኩራት ከፍ ብላችኋል፣ **ያዕቆ.** ፪፥፲፫፣ ፲፮ (አልማ ፬፥፰–፲፪)። ከኩራታችሁስ ተገፍፋችኋልን፣ **አልማ** ፭፥፳፰። በህዝቡ ልብ ውስጥ ታላቅ ኩራት ገባ፣ **ሔለ.** ፫፥፴፫–፴፮። በኩራት ለመወጠር ምንኛ ፈጣን ናቸው፣ **ሔለ.** ፲፪፥፬–፭። የዚህ ሀገር ኩራት እንደሚጠፉ አረጋግጦአል፣ **ሞሮኒ** ፰፥፳፯።

ኩራትን ተጠንቀቁ፣ አሊያም እንደ ኔፋውያን ትሆናላችሁ፣ **ት. እና ቃ.** ፴፰፥፴፱። ኩራታችሁን እና ተራ አስተሳሰባችሁን ሁሉ አቁሙ፣ **ት. እና ቃ.** ፹፰፥፻፳፩።

ኩነኔ። *ደግሞም* መንፈሳዊ ሞት፤ ሲዖል፤ የጥፋት ልጆች፤ ዲያብሎስ *ተመልከቱ*

ከማደግ መወገድና በእግዚአብሔርና በክብሩ ፊት ለመቅረብ መወገድ። ፍርድ (ኩነኔ) የሚገኘው በተለያዩ ደረጃዎች ነው። ሙሉ የሰለስቲያል ዘለአለማዊነትን የማያገኙት በሙሉ በእድገታቸው እና በመብቶቻቸው በትንሽም ደረጃ ይወገዳሉ፣ እና በዚህም መጠን የተፈረደባቸው (የኮነኑ) ናቸው።

እናንተ ግብዞች ወዮላችሁ፤ ስለዚህ የባሰ ፍርድ ትቀበላላችሁ፣ **ማቴ.** ፳፫፥፲፬። በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚሳደብ ሁሉ ግን የዘላለም ኃጢአት ዕዳ ይሆንበታል፣ **ማር.** ፫፥፳፱። ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉ፣ **ዮሐ.** ፭፥፳፱ (፫ ኔፊ ፳፮፥፭)። ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና፥ ይጠጣልምና፣ **፩ ቆሮ.** ፲፩፥፳፱ (፫ ኔፊ ፲፰፥፳፰–፳፱)።

ንስሀ የማይገቡ፣ እናም የማይጠመቁ፣ እና እስከመጨረሻው የማይጸኑ መኮነን ይገባቸዋል፣ **፪ ኔፊ** ፱፥፳፬ (ማር. ፲፮፥፲፮፤ ኤተር ፬፥፲፰፤ ት. እና ቃ. ፷፰፥፱፤ ፹፬፥፸፬)። ክፉዎች ከእግዚአብሔር ጋር መኖር ከተኮነኑት ነፍሳት ጋር በሲዖል ከመኖር በላይ አሰቃቂ ነው፣ **ሞር.** ፱፥፬።

እስከሚታዘዝ ድረስ ምንም የማያደርገው፣ እርሱም የተኮነነ ነው፣ **ት. እና ቃ.** ፶፰፥፳፱። አዲስ እና ዘለአለማዊ ቃል ኪዳንን ሙላት የሚቀበልም በህጉ ይኑር፣ ወይም ይኮነናል፣ **ት. እና ቃ.** ፻፴፪፥፮።

ኪምባል፣ ስፔንሰር ደብሊው። *ደግሞም* አስተዳደሪያዊ አዋጅ ፪ *ተመልከቱ*

ቤተክርስቲያኗ በ፲፰፻፴ (እ.አ.አ.) ከተመሰረተች በኋላ አስራ ሁለተኛው ፕሬዘደንት። ስፔንሰር ደብሊው ኪምባል ከ፲፱፻፸፫ እስከ ፲፱፻፹፭

(እ.አ.አ.) እንደ ፕሬዘደንት አገለገሉ። የተወለዱት በ፲፰፻፶፭ (እ.አ.አ.) ነበር እና በ፶ አመታቸው በ፲፱፻፹፫ (እ.አ.አ.) ሞቱ።

በሰኔ ፲፱፻፹፰ (እ.አ.አ.)፣ ቀዳሚ አመራር የክህነት መብትን እና የቤተመቅደስ በረከቶችን ብቁ ለሆኑ ወንዶች ሁሉ የሚዘረጋ ራዕይ ፕሬዘደንት ኪምባል እንደተቀበሉ አስታወቀ፣ **አ.አ.** ፪።

ኪሩቤል

የሰማይ ፍጥረቶችን የሚወክሉ ቅርጾች፣ ትክክለኛው አመለካከታቸው አይታወቅም። ኪሩቤል ቅዱስ በታዎችን ለመጠበቅ ተጠርተዋል።

ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውንም መንገድ ለመጠበቅ ኪሩቤልን አስቀመጠ፣ **ዘፍጥ.** ፫፡፳፬ (አልማ ፲፪፡፳፭–፳፱፣ ፵፪፡፪–፫)። በምህረት መቀመጫ ላይ በምሳሌ የሚወክሉ ኪሩቤል ተቀምጠው ነበር፣ **ዘፀአ.** ፳፭፡፲፰፣ ፳፪ (፩ ነገሥ. ፮፡፳፫–፳፰፣ ዕብ. ፱፡፭)። ኪሩቤል በሕዝቅኤል ራዕዮች ውስጥ ተጠቅሰዋል፣ **ሕዝ.** ፲፣ ፲፩፡፳፪።

ኪዳን። ብሉይ ኪዳን፣ አዲስ ኪዳን *ተመልከቱ*

ካህን፣ የመልከ ጼዴቅ ክህነት። *ደግሞም* ሊቀ ካህን፣ የመልከ ጼዴቅ ክህነት *ተመልከቱ*

በእግዚአብሔር በፊት የሀይማኖት ስርዓትን ለሌሎች የሚያከናውን ሰው። በብዙ ጊዜ በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ፣ ካህናት እንደ መልከ ጼዴቅ ስርዓት ሊቀ ካህናት ናቸው (አልማ ፲፫፡፪)። ከት ንሳኤ በኋላ የእግዚአብሔርን ክብር ሙሉነት የሚቀበሉት በሰለስቲያል መንግስት ውስጥ ካህናትና ንጉሶች ይሆናሉ።

መልከ ጼዴቅም የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበረ፣ **ዘፍጥ.** ፲፬፡፲፰። እንደ መልከ ጼዴቅ ሥርዓት አንተ ለዘላለም ካህን ነህ፣ **መዝ.** ፻፲፡፬ (ዕብ. ፭፡፮፣ ፯፡፲፯፣ ፳፩)።

ክርስቶስ ለአምላኩና ለአባቱ ካህናት እንድንሆን አደረገ፣ **ራዕ.** ፩፡፮ (ራዕ. ፭፡፲፣ ፳፡፮)።

ጌታ እግዚአብሔር ካህናት እንደ ቅዱስ ስርዓቱ እንደሾመ አስታውሱ፣ **አልማ** ፲፫፡፩–፳።

በጻድቅ ትንሳኤ የሚመጡት ካህናት እና ንጉሶች ናቸው፣ **ት. እና ቃ.** ፷፯፡፣ ፶፭–፳።

ካህን፣ የአሮናዊ ክህነት። *ደግሞም* ሊቀ ካህን፣ አሮናዊ ክህነት፣ አሮን፣ የሙሴ ወንድም *ተመልከቱ*

በአሮናዊ ክህነት ውስጥ የሚገኝ ሀላፊነት። በጥንት፣ በሌዋውያን ክህነት ውስጥ በአሮንና በትውልዶቹ ይያዙ የነበሩ ከፍተኛ ሀላፊነቶች። ክርስቶስ የሙሴ ህግን ሲያሟላ፣ ይህ ገደብ ተነስቷል።

ዳግም በተመለሰችው ቤተክርስቲያኗ ውስጥ የካህናት ሀላፊነቶች ተገልጸዋል፣ **ት. እና ቃ.** ፳፡፶–፶፪።

ካሌብ

ከስደት ከሁለት አመት በኋላ የከነዓንን ምድር እንዲፈትሽ በሙሴ ከተላኩት አንዱ። እርሱ እና ኢያሱ ብቻ ስለምድሩ እውነተኛ ሀተታ አመጡ (ዘኁል. ፲፫፡፮፣ ፴፣ ፲፬፡፮–፴፰)። ከግብፅ ከወጡት እነርሱ ብቻ በምድረበዳው ውስጥ ለአርባ አመታት ተረፉ (ዘኁል. ፳፮፡፳፭፣ ፴፪፡፲፪፣ ዘዳግ. ፩፡፴፮) እናም ወደ ከነዓን ገቡ (ኢያ. ፲፬፡፮–፲፭፣ ፲፭፡፲፫–፲፱)።

ካም። *ደግሞም* ኖኅ፣ የመፅሐፍ ቅዱስ የአባቶች አለቃ *ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የኖህ ሶስተኛ ወንድ ልጅ (ዘፍጥ. ፭፡፴፪፣ ፮፡፲፣ ሙሴ ፰፡፲፪፣ ፳፯)።

ኖህ፣ ወንድ ልጆቹ፣ እና ቤተሰቦቻቸው ወደ መርከቡ ገቡ፣ **ዘፍጥ.** ፯፡፲፫። የካም ልጅ ከነዓን ተረገመ፣ **ዘፍጥ.** ፱፡፲፰–፳፭።

የካም መንግስት ከአባት ወደ ወንድ ልጅ የሚተላለፍ ነበር እናም በምድራዊ ነገሮችና በጥበብ ቢባረክም በክህነት ስልጣን የተባረከ አልነበረም፣ **አብር.** ፩፡፳፭–፳፯። የካም ባለቤት፣ ግብፅዎስ፣ የቃየን ትውልድ ነበረች፣ የሴት ልጃቸው ግብፅዎስ ወንድ ልጆች በግብፅ ውስጥ ሰፈሩ፣ **አብር.** ፩፡፳፫፣ ፳፭ (መዝ. ፻፭፡፳፫፣ ፻፯፡፳፭–፳፱)።

ካሳ፣ ዳግም መመለስ። *ደግሞም* የወንጌል ዳግም መመለስ *ተመልከቱ*

ተወስዶ የነበረ ወይም የጠፋ ነገር ወይም ሁኔታ መመለስ።

መንፈስና ሰውነት በፍጹም ሁኔታ ደግመው ይገናኛሉ፣ **አልማ** ፲፩፡፴፫–፴፬። ዳግም መመለስ ክፉን ለክፉ፣ ጻድቅን ለጻድቅ ማምጣት ነው፣ **አልማ** ፴፩፡፲–፲፭።

በአስሩ ጎሳዎች ዳግም መመለስ እናም ምድርም ታድሳ እንደገነነት አይነት ክብር እንደምትቀበልም እናምናለን፣ **እ.አ.** ፩፡፲ (ት. እና ቃ. ፻፴፫፡፳፫–፳፬)።

ካስማ

ከኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ድርጅቶች እና ማስተዳደሪያ ክፍል አንዱ። ካስማ በብዙ ዎርዶች ወይም ቅርንጫፎች የተሰራ ነው። በኢሳይያስ ፶፬፡፪ ውስጥ "አውታሮ ችሽን አስረዝሚ ካስሞችሽንም አጽኚ" በማለት የድንኳን ምስልን እንደገለጸው፣ ይህም የተመደበ የቦታዎች ገደብ ያለው ነው። ካስማ ለተበተኑት እስ

ራኤል ቅሪዎች መሰብሰቢያ ቦታ ነው (ት. እና ቃ. ፲፪፡፲፫–፲፬፣ ፤ ፤ ፲፯–፳፩)።

ካስማዎችሽን አጥብቂ እናም ወሰንሽንም ለዘለዓለም አስፊ፣ ሞሮኒ ፤ ፡ ፤ ፤ (ት. እና ቃ. ፲፪፡፲፬)።

ከዚህ በላይ ሌላ ካስማ በፅዮን እንድትመድብ፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ ። በፅዮን ምድርና በካስማዎቿ ላይ አብሮ መሰብሰቡ ለመሸሸጊያ እንዲሆን ነው፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ (ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ ፤)። ለካስማዎች ሌሎች ቦታዎች ይመደባሉ፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ ። የሊቀ ካህናት ቡድን ፕሬዘደንቶች የሚመደቡት የካስማ ፕሬዘደንት እንዲሆኑ የሚመደቡትን ብቁ ለማድረግ ነው፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ ፤ ፡ ፤ ። ካስማዎቿ እንደጠናከሩ ዘንድ፣ ወደ ፅዮን ምድር ሂዱ፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ ።

ካውደሪ፣ ኦልቨር

ዳግም የተመለሰችው ቤተክርስቲያን ሁለተኛ ካህን እና ለመፅሐፈ ሞርሞን መለኮታዊ ስረ ነገርና እውነተኛነት ምስክር ከሆኑት ከሶስቱ አንዱ። ጆሴፍ ስሚዝ መፅሐፈ ሞርሞንን ከወርቅ ሰሌዳዎች ሲተረጎም እንደ ጸሀፊ አገለገለ (ጆ.ስ.—ታ. ፤ ፡ ፤ ፤–፤ ፤)።

ስለመፅሐፈ ሞርሞን ትርጉም እውነትነት ምስክር ተቀበለ፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ ፤ ፤ ፡ ፤ ።

በመጥቁዑ ሶሐንስ ተሾመ፣ ት. እና ቃ. ፤ ። (ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ ፤ ፤ ። ጆ.ስ.—ታ. ፤ ፡ ፤ ፤–፤ ፤ ። የቁጥር ፤ ፤ ማስታወሻን ተመልከቱ)። እውነትን ካገኘህ እና በአይኖችህ ካየሀቸው በኋላ፣ እንዳየሀቸው ትመሰክራለህ፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ ። በመንፈሴ የጻፍካቸው እውነት እንደሆኑ ለአንተ ገልጬልሀለሁ፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ ። በራዕያት ላይ ከመጋቢዎቹ አንዱ እንዲሆን ተመድቧልም ተሾሟልም፣ ት. እና ቃ. ፤ ። ከጆሴፍ ስሚዝ ጋር የክህነት ቁልፎችን ተቀብሏል፣ ት. እና ቃ. ፤ ።

ኬብሮን

ከኢየሩሳሌም በሰላሳ ሁለት ኪሎ ሜትር ወደ ደቡብ አልፎ የሚገኝ የጥንት የይሁዳ ከተማ። የአብርሐም እና የቤተሰቡ መቃብር ቦታ ነበር (ዘፍጥ. ፡ ፤–፡ ፤)። በዳዊት የመጀመሪያ ዘመነ መንግስት ዋና ከተማውም ነበረ (፤ ሳሙ. ፤ ፡ ፤–፤)።

ክህነት

ደግምም ሀይል፣ መሾም፣ ሹመት፣ ስልጣን፣ አሮናዊ ክህነት፣ የመልከ ጼዴቅ ክህነት፣ የክህነት መሀላ እና ቃል ኪዳን፣ የክህነት ቁልፎች ተመልከቱ

ለሰው ደህንነት በሁሉም ነገሮች ሰዎች ለመስራት እንዲችሉ እግዚአብሔር ለሰው የሚሰጠው ስልጣን እና ሀይል (ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤–፤)። የክህነት ባለስልጣን የሆኑ የቤተክርስቲያኗ ወንድ አባላት በቡድኖች ተደራጅተዋል እናም በቤተክርስቲያኗ ውስጥ ስነስርዓቶችንና ማስተዳደሪያ ስራዎችን ለማከናወን ስልጣን አላቸው።

መቀባታቸውም ለዘላለም ክህነት ይሆንላቸዋል፣ ዘፀአ. ፡ ፤ ፤ (ዘኁል. ፤ ፡ ፤ ፤)።

ሾምኋችሁ፣ ዮሐ. ፤ ፡ ፤ ። ቅዱሳን ካህናት እንድትሆኑ መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተሠሩ፣ ፤ ጴጥ. ፤ ፡ ፤ ። እናንተ የጠራችሁን ትውልድ የንጉሥ ካህናት ናችሁ፣ ፤ ጴጥ. ፤ ፡ ፤ (ዘፀአ. ፤ ፡ ፤)።

በእምነታቸው እና በታላቅ ስራቸው ምክንያት ሰዎች እንደ ሊቀ ካህናት ተጠርተዋል፣ ኦልማ ፤ ፡ ፤–፤ ። እንድታጠምቅ ስልጣንን እሰጥሃለሁ፣ ፤ ኔፊ ፤ ፡ ፤ ። መንፈስ ቅዱስንም ለመስጠት ስልጣን ይኖራችኋል፣ ሞሮኒ ፤ ፡ ፤ ።

በኤሊያስ እጅ ክህነትን እገልጽላችኋለሁ፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ (ጆ.ስ.—ታ. ፤ ፡ ፤ ፤)። ጌታ ክህነትን በአሮን እና በዘሮቹ ላይ አረጋገጠ፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ ። ይህም ታላቅ ክህነት ወንጌሉን ያስተዳድራል፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ ። ሙሴን፣ እናም ደግሞም ቅዱስ ክህነትን፣ ከመካከላቸው አወጣ፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ ። የክህነት መሀላ እና ቃል ኪዳን ተገልጿል፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤–፤ ። በአባቶቻችሁ ዘር ክህነት ቀጥለዋል፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ ። በቤተክርስቲያኗ ውስጥ፣ ሁለት የክህነት ባለስልጣኖች አሉ፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ ። የመጀመሪያው ክህነት፣ እንደ እግዚአብሔር ልጅ ስርዓት ቅዱስ ክህነት ነው፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤–፤ ። የክህነት መብቶች እና የሰማይ ሀይሎች የማይነጣጠሉ ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ ። በማሳመን እና ግብዝነት በሌለው ፍቅር ካልሆነ በስተቀር፣ ምንም ሀይል ወይም ተጽዕኖ በክህነት ስልጣን ዘዴ ሊደገፍ አይቻልም ወይም አይገባም፣ ት. እና ቃ. ፤ ፡ ፤ ። እያንዳንዱ ታማኝ፣ ብቁ ወንድ የቤተክርስቲያኗ አባል ክህነትን ይቀበላል፣ ኢ.ኢ. ፤ ።

ወንድ በእግዚአብሔር መጠራት አለበት፣ ኢ.ኢ. ፤ ፡ ፤ ።

ክህደት

ደግምም አመጽ፣ የወንጌል ዳግም መመለስ ተመልከቱ

በግለሰቦች፣ በቤተክርስትያን፣ ወይም በሕዝቦች ሁሉ ከእውነት ዞር ማለት።

ታላቅ ክህደት፣ እስራኤል ከጌታ ልቦቻቸው ከሚያስቱት ይጠብቁ፣ ዘዳግ. ፡ ፤ ፤ ። ራዕይ ባይኖር ሕዝብ መረን ይሆናል፣ ምሳ. ፡ ፤ ፤ ። የዘላለሙንም ቃል ኪዳን አፍርሰዋል፣ ኢሳ. ፡ ፤ ። ነፋስም ነፈሰ ያንም ቤት መታው፣ ወደቀም፣ ማቴ. ፤ ፡ ፤ ። ወደ ልዩ ወንጌል እንዲህ ፈጥናችሁ እንዴት እንዳለፋችሁ እደነቃለሁ፣ ገላ. ፤ ፡ ፤ ።

በጥሩ መንገድ ጉዞ ጀመሩ፣ ነገር ግን መንገዳቸውን በጭጋግ ውስጥ ሳቱ፣ ፤ ኔፊ ፡ ፤ ፤ (፤ ኔፊ ፤ ፡ ፤ ፤)። ፍሬውን ከቀመሱ በኋላ አፈሩ፣ ወደ ተከ

ለከለውም መንገድ ገቡና ጠፉ፣ ፤ ኔሬ ፯፡፯፯፡፡ የኔፋውያን ክህደት ለማያምኑት መደናቀፊያ ሆነ፣ አልማ ፱፡፤–፲፪፡፡ የቤተክርስቲያና አባላት በኩራት ተወጠሩ እናም ሌሎች አባላትን አሳደዱ፣ ሔሌ. ፫፡፴፫–፴፱ (ሔሌ. ፱፡፲፭–፲፫፣ ፭፡፪–፫)። ጌታ ህዝቡን ሲያበለፅግ፣ አንዳንዴ እነርሱ ልባቸውን ያጠጥራሉ እናም ይረሱታል፣ ሔሌ. ፲፪፡፪፣ ፲፫፡፴፯፡፡ ኔፋውያን ልባቸውን አደነደኑ እናም በሰይጣን ሀይል ስርም ወደቁ፣ ፫ ኔሬ ፪፡፭–፫። ሞሮኒ ስለመጨረሻው ቀናት ክህደት ተነበየ፣ ሞር. ፯፡፯፯፣ ፴፭–፴፭።

ከዳግም ምፅዓት በፊት ክህደት ይመጣል፣ ት. እና ቃ. ፭፡፲፫–፲፮።

የመጀመሪያ የክርስትያን ቤተክርስትያን ክህደት፣ ይህ ሕዝብ በአፉ ወደ እኔ ይቀርባል፣ ኢሳ. ፳፱፡፣ ፲፫። ጨለማ ምድርን ይሸፍናል፣ ኢሳ. ፮፡፪። ጌታ የእግዚአብሔርን ቃላትን የመስማት ራብን ይልካል፣ ዓሞ. ፰፡፲፭።

ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉ፣ ማቴ. ፳፬፡፳፬። ጨካኞች ተኩላዎች በመካከላችሁ ይገባሉ፣ የሐዋ. ፳፡፳፱። ወደ ልዩ ወንጌል እንዲህ ፈጥናችሁ እንዴት እንዳለፋችሁ እደነቃለሁ፣ ገላ. ፩፡፮። ከዳግም ምፅአት በፊት ክህደት አስቀድሞ ይመጣል፣ ፪ ተሰ. ፪፡፫። አንዳንዶች ስለ እውነት ይስታሉ፣ ፪ ጢሞ. ፪፡፲፰። አንዳንዶች የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ይክዳሉ፣ ፪ ጢሞ. ፫፡፪–፭። እውነት ትምህርትን የማይጸኑበት ጊዜ ይመጣል፣ ፪ ጢሞ. ፬፡፫–፬። ሐሰተኞች ነቢያት እና ሐሰተኞች በህዝቡ መካከል፣ ፪ ጴጥ. ፪፡፩። አንዳንዶች ሰዎች ሾልከው ብቻውን ያለውን ንጉሳችንን እና ጌታችንን ይክዳሉ፣ ይሁዳ ፩፡፬። አንዳንድ ሰዎች ሐዋርያት ነን ይላሉ እና አይደሉም፣ ራዕ. ፪፡፪።

ኔሬ የታላቋና የርኩሰቱን ቤተክርስቲያን መመስረትን አየ፣ ፤ ኔሬ ፲፫፡፳፯። አህዛብ ተሰናክለዋል እና በዚህም ብዙ ቤተክርስቲያኖች ሰርተዋል፣ ፪ ኔሬ ፳፯፡፳።

ከስርዓቴ እርቀዋል፣ እናም የዘላለማዊ ቃል ኪዳኔን አፍርሰዋልና፣ ት. እና ቃ. ፩፡፲፭። ጭለማ ምድርን፣ እና ታላቅ ጭለማም የህዝቦችን አዕምሮ ሸፍኗል፣ ት. እና ቃ. ፲፲፪፡፳፫።

ጆሴፍ ሁሉም ቤተክርስቲያናት ስህተተኛ እስ ደሆኑ ተነገረው፣ ልባቸውም ከእግዚአብሔር የራቁ ነበሩ፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፲፱።

ክርስቲያኖች። *ደግሞም ቅዱሳን፣ ደቀ መዛሙርት ተመልከቱ*

በኢየሱስ ክርስቶስ ለሚያምኑት የተሰጠ ስም ምንም እንኳን ይህ ስም በአለም ውስጥ ሁሉ የሚ ጠቀመበት ቢሆንም፣ ጌታ የክርስቶስ ተከታዮችን እንደ ቅዱስን መድቧቸዋል (የሐዋ. ፱፡፲፫፣ ፴፪፣ ፴፩፣ ፩ ቆሮ. ፩፡፪፣ ት. እና ቃ. ፲፲፭፡፬)።

ደቀ መዛሙርትም ክርስቲያኖች ተባሉ፣ የሐዋ. ፲፩፡፳፮። ክርስቲያን እንደሚሆን ግን መከራን ቢቀበል አይፈር፣ ፩ ጴጥ. ፬፡፲፮።

በቃል ኪዳን ምክንያት እናንተ የክርስቶስ ልጆች ትባላላችሁ፣ ሞዛያ ፭፡፯። በእውነት የሚያምኑት በቤተክርስቲያና አባል ባልሆኑት ክርስቲያን ተብለው ተጠሩ፣ አልማ ፴፯፡፲–፲፮።

ክርስቶስ። ኢየሱስ ክርስቶስ *ተመልከቱ*

ክርስቶስ ስለተባረኩ የተናገራቸው አረፍተ ነገሮች። *እርካታ ተመልከቱ*

ክብር። *ደግሞም መቆጠር፣ ማክበር፣ ብርሀን፣ የክርስቶስ ብርሀን፣ እውነት፣ የክብር ደረጃዎች ተመልከቱ*

በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ፣ ክብር ስለእግዚአብሔር ብርሀንና እውነት የሚያመለክት፣ ለአንድ ሰው ወይም ለአንድ ነገር አምልኮን ማሳየት ነው። ይህም ደግሞ ስለ ሙገሳ ወይም ክብር እናም ስለዘ ለአለማዊ ህይወት አንዳንድ ጉዳዮች ወይም ስለእ ግዚአብሔር ክብር ያመለክታል።

አባትህንና እናትህን አክብር፣ ዘፀአ. ፳፡፲፪ (፤ ኔሬ ፲፯፡፹፭፣ ሞዛያ ፲፫፡፳)። እግዚአብሔርን ከሀብትህ አክብር፣ ምሳ. ፫፡፱። ቅዱስ፣ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፣ ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞል ታለች፣ ኢሳ. ፮፡፫ (፪ ኔሬ ፲፯፡፫)።

የሚያገለግለኝም ቢኖር አብ ያከብረዋል፣ ዮሐ. ፲፪፡፳፮። እኛም ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን፣ ፪ ቆሮ. ፫፡፲፰። ባሎች ለሚስቶቻቸው ክብር ይስጧቸው፣ ፤ ጴጥ. ፫፡፯።

በከንፈሮቻቸውም ጌታን አከበሩ፣ ፪ ኔሬ ፳፯፡፳፭ (ኢሳ. ፳፱፡፲፫)። በክብር ከእርሱ ጋር እንድኖር በመጨረሻው ቀን ያስነሳኛል፣ አልማ ፴፯፡፳፯። የዓለምን ክብር አይደለም የምፈልገው፣ አልማ ፲፡፴፡፡

ኃይሌ የሆነውን ክብርህን ስጠኝ በማለት ዲያ ብሎስ በእኔ ላይ አመጸ፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፴፯። ታማኝ በክብር ዘውድ አክሊልም ይጫንላችኋል፣ ት. እና ቃ. ፫፲፭፡፭ (ት. እና ቃ. ፲፳፬፡፲፭)። ጌታ የሚያገለግሉትንም ለማክበር ይደሰታል፣ ት. እና ቃ. ፫፲፭፡፭። በትንሳኤ የምንቀበለው ክብር በጽድቅ መሰረት ይለያያል፣ ት. እና ቃ. ፫፲፭፡፱–፲፲፱። ፴፭ የእግዚአብሔር ክብር የመረዳት ችሎታ ነው፣ ት. እና ቃ. ፶፫፡፴፭። ያልተመረጡት በሰዎች ለመከበር ስለሚነሳሱ ነው፣ ት. እና ቃ. ፲፳፭፡፴፪–፴፭።

የሰውን ህያውነት እና ዘለአለማዊ ህይወት አምጥ ቶም ማሳለፍ የእግዚአብሔር ስራ እና ክብር ነው፣

ሙሴ ፩፡፴፱። ብርሀናቸውና ክብራቸው የሚገለጽበት ሁሉ ብቁ ያልሆነ፣ ሁለት ሰዎች በአየር ከእኔ በላይ ቆመው አየሁ፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፲፯። ህግን በማክበርና በመደገፍ እናምናለን፣ እ.አ. ፩፡፲፪ (ት. እና ቃ. ፲፴፰፡፯)።

ክንድ

በዕብራውያን መካከል የርዝመት መመዘኛ፣ በመጀመሪያ ከክርን እስከ ጣቶች ጫፍ ያለው ርዝመት ነበር።

ክፉ፣ ክፋት። *ደግሞም ኃጢያተኛ፣ አመፃ፣ ኃጢያት፣ መንፈሳዊ ጭለማ፣ እድፍ፣ እድፍነት፣ እግዚአብሔርን የሚጠላ ተመልከቱ*

ክፋት፣ ኃጢያት፣ ለእግዚአብሔር ትእዛዛት ታዛዥ አለመሆን።

እንዴት ይህን ትልቅ ክፉ ነገር አደርጋለሁ፣ ዘፍጥ. ፴፱፡፯–፱። እግዚአብሔር ከጎጥአን ይር ቃል፣ የጻድቃንን ጸሎት ግን ይሰማል፣ ምሳ. ፲፭፡፳፱። ጎጥአን በሠለጠኑ ጊዜ ግን ሕዝብ ያለ ቅሳል፣ ምሳ. ፳፱፡፪ (ት. እና ቃ. ፣፲፰፡፱)።

በውጭ ባሉቱ ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል። ክፉውን ከመካከላችሁ አውጡት፣ ፩ ቆሮ. ፭፡፲፫። መጋደላችን ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው፣ ኤፌ. ፣፡፲፪።

ከክፉዎች ውጡ እናም ተለዩ፣ እናም የጎ ደፉ ነገሮቻቸውን አትንኩ፣ **አልማ** ፭፡፲፯–፲፯ (ት. እና ቃ. ፴፣፡፣)። የኃጢአተኞች የመጨረሻ ሁኔታ ይህ ነው፣ **አልማ** ፴፬፡፴፭ (አልማ ፣፡፣–፣፡)። ክፋት በፍፁም ደስታ ሆኖ አያውቅም፣ **አልማ** ፣፡፣፡፣። ኃጥአን የሚቀጡት በኃጢአተኞች ነው፣ **ሞር.** ፬፡፭ (ት. እና ቃ. ፣፣፡፡፡፴)።

በእዚያም ሰዓት ጻድቃኖችን ከጎጥያተኞቹ በሙሉ የሚለያዩበት ይመጣል፣ ት. እና ቃ. ፣፣፡፡፡፣፡።

እንደዚህም የክፉዎች መጨረሻ ይመጣል፣ ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፡፣፣፩።

ክፉ መናገር። *ደግሞም ሐሰት፣ አሉባልታ፣ ወሬ፣ ጸብ ተመልከቱ*

ትክክል ያልሆኑ፣ የሚጎዱ፣ እና ክፉ የሆኑ ነገሮችን መናገር። በብዙ ጊዜ በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ እንደዚህ አይነት ንግግር የሚደረገው በሰው ላይ ጉዳት ለማምጣት ነው።

አንደበትህን ከክፉ ከልክል፣ መዝ. ፴፬፡፲፫ (፩ ጴጥ. ፫፡፣)። ምናምንቴ ሰው ክፋትን ይም ሳል፣ ምሳ. ፲፣፡፣፭፣። ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ፣ ማቴ. ፭፡፲፩ (፫ ኔፊ ፲፪፡፲፩)። ከልብ ክፉ አሳብ ይወጣል፣ ማቴ. ፣፭፡፣፣ (ማር. ፣፡፣፭፩)። በሕዝብህ አለቃ ላይ ክፉ ቃል አትና ገር፣ የሐዋ. ፳፫፡፭። ክፉ ንግግሮች ሁሉ ከእና ንተ ዘንድ ይወገድ፣ ኤፌ. ፬፡፴፩። እርስ በርሳችሁ አትተማሙ፣ ያዕ. ፬፡፣፩።

መተማማት፣ ወይም ክፉ መነጋገር እንዳይኖር ይጠበቅ፣ ት. እና ቃ. ፭፡፣፬።

ክፉ መንፈሶች። *መንፈስ—ክፉ መንፈሶች ተመልከቱ*

ወሊድ መቆጣጠሪያ። *ደግሞም ቤተሰብ፣ ጋብቻ፣ መጋባት ተመልከቱ*

ፅንስን በመቆጣጠር ወይም በመከላከል ለተጋቡት የሚወለዱትን ልጆች ቁጥር መቆጣጠር።

ብዙ፡ ተባዙ፡ ምድርንም ሙሉአት፣ ዘፍጥ. ፩፡፳፰ (ሙሴ ፪፡፳፰)። ልጆች የእግዚአብሔር ቅርስ ናቸው፣ መዝ. ፲፳፯፡፣–፫።

የሌሒ ቤተሰብ ለጌታ ዘር ያሳድጉ፣ ፩ ኔፊ ፣፡፩።

ጋብቻ ለሰው በእግዚአብሔር የተመደበ ነው፣ ት. እና ቃ. ፴፱፡፣፭–፣፣። ከፍ ከፍ ያሉት ሙሉ ነትን እና የዘር ቀጣይነትን ለዘለአለም ይቀበላሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፴፪፡፣፱፣ ፣፣፫።

ወላጆች። *ደግሞም ሚች አባት፣ እናት ተመልከቱ*

አባቶችና እናቶች። በእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ውስጥ በትክክለኛው ስርዓት በጋብቻ የተሳሰሩ ብቁ ባሎች እና ሚስቶች የወላጅነት ሀላፊነታቸውን በዘለአለም ሁሉ ያሟላሉ። “ወላጆች ልጆቻቸውን በፍቅር እና በጽድቅ የማሳደግ፣ ስጋዊ እና መንፈሳዊ ፍላጎታቸውን የማሟላት፣ እና እርስ በራስ እንዲዋደዱና እንዲያገለግሉ፣ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት እንዲያከብሩ፣ እና በሚኖሩበት በማንኛውም ቦታ ህግን የሚያከብሩ ዜጋዎች እንዲሆኑ የማስተማር ቅዱስ ሀላፊነት አላቸው” (“ቤተሰብ፡ ለአለም የተላለፈ አዋጅ”፣ *Ensign,* ህዳር ፳፻፲ [እ.አ.አ.]፣ ፲፳፱)።

ልጆች ሆይ፡ ለወላጆቻችሁ ታዘዙ፣ ኤፌ. ፣፡፩–፫ (ቁላ. ፫፡፳)።

አዳምና ሔዋን የመጀመሪያ ወላጆች ናቸው፣ ፩ ኔፊ ፭፡፣፩። እርግማኑ በወላጆቻችሁ ራስ ላይ ይመለስ፣ ፪ ኔፊ ፬፡፣። ወላጆች ንሰሃ መግባት እናም መጠመቅ እንዳለባቸው አስተምራቸው፣ ሞሮኒ ፰፡፣።

ወላጆች ልጆቻቸውን ወንጌል እንዲያስተምሩ ታዘዋል፣ ት. እና ቃ. ፰፰፡፰፭። ሁሉም ልጆች በወላጆቻቸው ላይ የመደገፍ መብት አላቸው፣ ት. እና ቃ. ፹፫፡፬።

የወላጆች ኃጢያት በልጆች ጭንቅላት ላይ አይ መለስም፣ ሙሴ ፮፡፱፬።

ወራሽ

ስጋዊ ወይም መንፈሳዊ ስጦታዎችን ለመውረስ መብት ያለው ሰው። በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ፣ ቅዱሳን እግዚአብሔር ላለው ሁሉ ወራሽ እንደ ምሚሆኑ ቃል ተገብቶላቸዋል።

አብርሐም ወራሽን ፈለገ፣ ዘፍጥ. ፲፭፡፪–፭።
አብርሃም የዓለምም ወራሽ የሆነው በእምነት ጽድቅ ነው፣ ሮሜ ፬፡፲፫። የእግዚአብሔር ልጆች ነን፣ ልጆች ከሆንን ወራሾች ደግሞ ነን፣ ማለት የእግዚአብሔር ወራሾች ነን፡ ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን፣ ሮሜ ፰፡፲፮–፲፯ (ት. እና ቃ. ፹፬፡፴፰)። ልጅ ነህ፣ በክርስቶስ የእግዚአብሔር ወራሽ ነህ፣ ገላ. ፬፡፯። እግዚአብሔር ልጁን የሁሉን ወራሽ አደረገ፣ ዕብ. ፩፡፪።
ለኃጢአታቸው ስርየት ያንን ቀን የሚጠብቁ፣ የእግዚአብሔርን መንግስት ወራሾች ናቸው፣ ሞዛያ ፲፭፡፲፩። ሰዎች በአንድነት የክርስቶስ ልጆች፣ እናም የእግዚአብሔርንም መንግስት ወራሾች ነበሩ፣ ፬ ኔፊ ፩፡፲፯።
ይህን ወንጌል ሳያውቁ የሞቱት ሁሉ የእግዚአብሔር ሰለስቲያል መንግስት ወራሾች ይሆናሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፱፯፡፣–፰። ንስሀ የገቡ ሙታን የደህንነት ወራሾች ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፲፱፯፡፱፰–፱፱።
አብርሐም በጽድቅ መብት ያለው ወራሽ ሆነ፣ አብር. ፩፡፪።

ወሬ። *ደግሞም አሉባልታ፤ ክፉ መናገር ተመልከቱ*

አንዳንዴም በግማሽ እውነት፣ ህዝብን ከእግዚአብሔር እና ከሁሉም ጥሩ ነገሮች ለማዞር ሰይጣን ወሬን እና ጸብን ያባዛል (ሔሌ. ፲፮፡፳፪፤ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፩)። የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት አንደኛው ምልክት ሰዎች ስለጦርነቶች እና ስለጦርነቶች ወሬ መስማታቸው ነው (ማቴ. ፳፬፡፮፤ ት. እና ቃ. ፵፭፡፳፮፤ ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፡፳፫)

ወንድሞች፣ ወንድም። *ደግሞም ሰው፣ ሰዎች፤ ሴት፣ ሴቶች፤ እህት ተመልከቱ*

እንደ ሰማይ አባታችን ልጆች፣ ወንዶች እና ሴቶች ሁሉ መንፈሳዊ መንድሞችና እህቶች ናቸው። በቤተክርስትያኗ ውስጥ፣ ወንድ አባላት እና የቤተክርስትያኗ ጓደኞች ብዙ ጊዜ ወንድም ተብለው ይጠራሉ።

አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አጽና፣ ሉቃ. ፳፪፡፴፪። ወንድሙን የማይወድ በሞት ይኖራል፣ ፩ ዮሐ. ፫፡፲–፲፯።

ወንድሞቻችሁን እንደ እራሳችሁ አስቡባቸው፣ ያዕቆ. ፪፡፣፲፯።
እያንዳንዱ ሰው ወንድሙን እንደ እራሱ ይመልከት፣ ት. እና ቃ. ፴፯፡፳፬–፳፭። በንግግራችሁ በሙሉ ወንድሞቻችሁን አጠናክሩ፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፣፯።

ወንጀል። በደል *ተመልከቱ*

ወንጌል። *ደግሞም ዘመን፤ የቤዛነት ዕቅድ፤ የክርስቶስ ትምህርት ተመልከቱ*

በኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢያት ክፍያ በኩል እንዴቻል የሆነ የእግዚአብሔር የደህንነት አላማ። ወንጌል ወደ እግዚአብሔር ፊት ለመመለስ የሰው ዘር የሚያስፈልጋቸውን የዘለአለም እውነቶች ወይም ህግጋት፣ ቃል ኪዳኖች፣ እና ስርዓቶች ያጠቃልላል። እግዚአብሔር በ፲፱ኛው መቶ አመት ውስጥ በነቢዩ ጆሴ ስሚዝ በኩል ሙሉ ወንጌልን በምድር ላይ በዳግም መለሰ።

ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ስበኩ፣ ማር. ፲፮፡፣፲፭።
ግልፅና እጅግ የከበረው የበጉ ወንጌል ክፍል ወደ ኋላ ተያዙ፣ ፩ ኔፊ ፲፣፡፣፴፪። ይህ ወንጌሌ ነው፣ ፫ ኔፊ ፳፯፡፣፲፣–፳፩ (ት. እና ቃ. ፴፱፡፣፯)።
መፅሐፈ ሞርሞን ሙሉ ወንጌልን ይዟል፣ ት. እና ቃ. ፳፡፣፳–፱ (ት. እና ቃ. ፵፪፡፣፲፪)። ይህ ወንጌል ነው፣ ት. እና ቃ. ፫፯፡፣፣–፵፣፣። የመልከ ጼዴቅ ክህነት ወንጌሉን ያስተዳድራል፣ ት. እና ቃ. ፹፬፡፣፲፱። የወንጌል ሙላትን በእራሱ ልሳን እያንዳንዱ ሰው ይሰማል፣ ት. እና ቃ. ፣፡፣፲፩። ወልድ ወንጌልን ለሙታን መንፈሶች ሰበከ፣ ት. እና ቃ. ፲፴፯፡፣፲፳–፳፭፣ ፳፳–፴፣፯።
ወንጌሉ ከመጀመሪያው ጊዜ ጀምሮ መሰበክ ጀመረ፣ ሙሴ ፩፡፣፲፳። የወንጌሉ ቀዳሚ መሰረታዊ መርሆችና ስነስርዓቶች ተገልጸዋል፣ ኤ.አ. ፩፡፲።

ወንጌል ሰባኪ። *ደግሞም የአባቶች አለቃ፣ ፓትሪያርክ፤ የፓትሪያርክ በረከቶች ተመልከቱ*

የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል መልካም ዜናን የሚያውጅ ወይም የሚወስድ ሰው። ጆሴፍ ስሚዝ ወንጌል ሰባኪ ፔትሪያርክ እንደሆነ አስተምሯል። ፔትሪያርኮች የተጠሩና በአስራ ሁለቱ ሐዋሪያት አመራር መሰረት የፔትሪያርክ በረከቶች ተብለው የሚጠሩ ልዩ በረከቶችን ለመስጠት የሚሾሙ ናቸው።

ጌታ አንዳንዶቹን ሐዋርያት፣ ሌሎቹን ነቢያት፣ ሌሎቹን ወንጌልን ሰባኪዎች እንዲሆኑ ሰጠ፣ ኤፌ. ፬፡፲፩። የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ አድርግ፣ ፪ ጢሞ. ፬፡፭።
በሀዋርያት፣ በነቢያት፣ በሚኒስትሮች፣ በአስተ

ማሪዎች፣ በወንጌል ሰባኪዎች እናምናለን፣ ኤ.አ. ፩፡፲፤

ወንጌሎች። *ደግሞም ሉቃስ፤ ማርቆስ፤ ማቴዎስ፤ ዮሐንስ፣ የዘብዴዎስ ልጅ ተመልከቱ*

የኢየሱስ ምድራዊ ህይወት እና የአገልግሎቱ ድርጊቶች ምስክሮችን የያዙ በአዲስ ኪዳን የመ ጀመሪያ አራት መፅሐፎች ውስጥ የሚገኙ አራት መዝገበች። የተጻፉትም በማቴዎስ፣ በማርቆስ፣ በሉቃስ፣ እና በዮሐንስ ነው፣ እነዚህም ስለክርስ ቶስ ህይወት የተመዘገቡ ምስክሮች ናቸው። በመ ፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ የሚገኘው ፫ ኔፊ መፅሐፍ በብዙ መንገዶች ከእነዚህ አዲስ ኪዳን ወንጌሎች ጋር የተመሳሰለ ነው።

የአዲስ ኪዳን መፅሐፎች በመጀመሪያ የተጻፉት በግሪክ ቋንቋ ነበር። በግሪክ ቋንቋ *ወንጌል* ማለት "መልካም ዜና" ማለት ነው። መልካሙም ዜና የሰው ዘርን በሙሉ ከሞት ለማዳን ኢየሱስ ክርስቶስ ለኃጢያት ዋጋ መክፈሉ እና እያንዳንዱን ለስራው ደመወዝ ናቸው። (ዮሐ. ፫፡፲፮፤ ሮሜ ፭፡፲–፲፩፤ ፪ ኔፊ ፱፡ሸ፲፤ አልማ ፴፪፡ፀ፤ ት.እና ቃ. ፳፯፡ሸ–ሸ፱)

የወንጌሎች ስምምነትን በተጨማሪ መግለጫ ውስጥ ተመልከቱ።

ወኪል። *ለሙታን ደህንነት፤ ስነስርዓቶች—የወኪል ስነስርዓት ተመልከቱ*

ወደ ሰማይ ማረግ። *ደግሞም ኢየሱስ ክርስቶስ፤ የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት ተመልከቱ*

ከትንስኤው አርባ ቀናት በኋላ፣ አዳኝ ከምድር የሄደበት። ወደ ሰማይ ማረጉ የነበረው በደቀ መዛ ሙርቶች ፊት ለፊት በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ነበር (ማር. ፲፮፡፲፱፤ ሉቃ. ፳፬፡ፀ፲ሸ)። በእዚያም ጊዜ ከሰማይ የመጡ ሁለት መላእክቶች ጌታ ወደ ፊት "እንዲሁ" ይመለሳል ብለው መሰከሩ (የሐዋ. ፩፡፱–፲፪)።

ወደ ሮሜ መልእክት። *ደግሞም የጳውሎስ መልእክቶች፤ ጳውሎስ ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ ጳውሎስ በሮሜ ላሉት ቅዱሳን የጻፈው ደብዳቤ። አደጋ ቢኖርበትም፣ ኢየ ሩሳሌምን ለመጎብኘት እያሰበ ነበር። በህይወቱ ካመ ለጠ፣ ከእዚያም በኋላ ሮሜን ለመጎብኘት ተስፋ ነበ ረው። ደብዳቤውን የጻፈው፣ እርሱ ሲመጣ እርሱን ለመቀበል በእዚያ ያለችው ቤተክርስቲያን እንድት ዘጋጅ ነበር። ይህም ክርክር የነበረባቸውን እና አሁን ጳውሎስ በመጨረሻ ተመስርተዋል ብሎ የተመለ ከታቸውን የአንዳንድ ትምህርቶች መረጃ እንደያዘ ሊታይበትም ይችላል።

ምዕራፍ ፩ ጳውሎስ ለሮሜ የላከውን ሰላምታ የያዘ ነበር። ምዕራፍ ፪–፲፩ የእምነት፣ ስራዎች፣ እና ጸጋ ትምህርት ብዙ አዋጆችን የያዙ ናቸው። ምዕራፍ ፲፪–፲፮ የፍቅር፣ የሀላፊነት፣ እና የቅዱስነት ትም ህርቶችን የያዙ ናቸው።

ወደ ቁላስይስ መልእክት። *ደግሞም የጳውሎስ መልእክቶች፤ ጳውሎስ ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያለ መፅሐፍ። ይህ በመ ጀመሪያ ሐዋሪያው ጳውሎስ በኤጳፍራ ከተጎ በኘ በኋላ ለቁላስይስ የጻፈው ደብዳቤ ነበር (ቁላ. ፩፡፣–፤)። ኤጳፍራ ጳውሎስን ቁላስይስ በከባድ ስህተት ውስጥ እየወደቁ እንዳሉ ነገረው—አን ዳንድ የውጪ ስነስርዓቶችን በጥንቃቄ ስለሚከ ተሉ (ቁላ. ፪፡፣–፲፮)፣ አንዳንድ ስጋዊ ፍላጎታቸ ውን ከእራሳቸው ስለሚያስወግዱ፣ እና መላእክ ትን ስለሚያመልኩ (ቁላ. ፪፡፲–ሸ)እነርሱ ከሌሎች ሰዎች የተሻሉ ይመስላቸው ነበር። እንዚህ ድር ጊቶች ቁላስይስን የተቀደሱ እንደሆኑ እንዲሰማ ቸው አደረጉአቸው። እነርሱም የሁለንታን ሚስ ጥሮች ከሌሎች የቤተክርስቲያን አባላት ይበልጥ እንደሚገባቸው ይሰማቸው ነበር። ቤዛነት የሚ መጣው በክርስቶስ ብቻ እንደሆነ እነርሱን በማ ስተካከል እና እኛ ጥበበኛ መሆን እንደሚገባን እና እንድናገለግለው በደብዳቤው ውስጥ ጳው ሎስ አስተማራቸው።

ምዕራፍ ፩ ጳውሎስ ለቁላስይስ የሰጠው ሰላምታ ነው። ምዕራፍ ፪–፫ ትምህርት የያዙ እናም ስለክር ስቶስ ቤዛነት፣ ስለሀሰት አምልኮ አደጋ፣ እና ስለ ትንሳኤ አስፈላጊነት መግለጫዎችን የያዙ ናቸው። ምዕራፍ ፬ ቅዱሳን በሁሉም ነገሮች ጠበበኛ መሆን እንዳለባቸው ያስተምራል።

ወደ ቆሮንቶስ መልእክት። *ደግሞም የጳውሎስ መልእክቶች፤ ጳውሎስ ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሁለት መፅሐፎች። እነዚህ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ለሚገኙት ቅዱሳን በመካከላ ቸው ያለውን ረብሻ ለማስተካከል የጻፈው ደብዳቤ ዎች ነበሩ። ቆሮንቶስ የኖሩት ክፉ በሆኑ ህብረተሰ ቦች ውስጥ ነበር።

መጀመሪያይቱ ቆሮንቶስ፣ ምዕራፍ ፩ የጳውሎስን ሰላምታና አንድ ስለመሆን የገሰጸባቸውን ይይዛል። ምዕራፍ ፪–፮ የቆሮንቶስ ቅዱሳን ስህተት ጳውሎስ ያስተካከላቸው ናቸው። ምዕራፍ ፯–፲፪ለአንዳንድ ጥያቄዎች የጳውሎስን መልስ የያዙ ናቸው። ምዕ ራፍ ፲፫–፲፭ በልግስና፣ በመንፈሳዊ ስጦታዎች፣ እና በትንሳኤ ላይ ያተኮሩ ናቸው። ምዕራፍ ፲፮ በእም ነት ጠንክረው እንዲቆሙ የጳውሎስን ምክር የያዙ ናቸው።

ሁለተኛይቱ ቆሮንቶስ፣ ምዕራፍ ፩ የጳውሎስን

ሰላምታና የመጽናናት መልእክት ይይዛል። ምዕራፍ ፤ ለቲቶ የግል ምክርን የያዘ ነው። ምዕራፍ ፫–፮ ወንጌል በቅዱሳንና በመሪዎቻቸው ህይወቶች ውስጥ ስላለው ሀይል ይናገራሉ። ምዕራፍ ፯–፱ ቅዱሳንን ለደህዎች በደስታ እንዲሰጡ ይመክራሉ። ምዕራፍ ፣–፲፤ ጳውሎስ ስለሐዋሪያነቱ የሚናገርባቸው ናቸው። ምዕራፍ ፲፫ ፍጹም ስለመሆን በትህትና የሚያስጠነቅቅ ነው።

ወደ ተሰሎንቄ መልእክት። *ደግምም የጳውሎስ መልእክቶች፤ ጳውሎስ ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያሉ ሁለት መጻህፍት። እነዚህ ጳውሎስ በ፶ ም.ዓ. አካባቢ አውሮፓን በጎበኘበት ጊዜ በቆሮንቶስ ውስጥ እያለ በመጀመሪያ ለተሰሎንቄ የጻፋቸው ደብዳቤዎች ነበሩ። በተሰሎንቄ የነበረው ስራ በ የሐዋርያት ስራ ፲፯ ውስጥ ተዘርዝረዋል። ጳውሎስ ወደ ተሰሎንቄ ለመመለስ ፈለገ ነገር ግን ይህን ለማድረግ አልቻለም ነበር (፩ ተሰ. ፪፡፣፲፰)። ስለዚህ የተቀየሩትን እንዲያስደስት እና እንዴት እንደሆኑ መልእክት እንዲያመጣለት ጢሞቴዎስን ላከ። ጳውሎስ የመጀመሪያውን መልእክት የጻፈው በጢሞቴዎስ መመለስ ምስጋና ስለተሰማው ነበር።

መጀመሪያይቱ ተሰሎንቄ፣ ምዕራፍ ፩–፪ የጳውሎስን ሰላምታ እና ለቅዱሳን ያለውን ጸሎት የያዙ ነበሩ፤ ምዕራፍ ፫–፭ ስለመንፈሳዊ እድገት፣ ፍቅር፣ ንጹህነት፣ ትጋት፣ እና ስለኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት መመሪያዎች የሚሰጡ ነበሩ።

ሁለተኛይቱ ተሰሎንቄ፣ ምዕራፍ ፩ ለቅዱሳን የነበረውን ጸሎት የያዘ ነበር። ምዕራፍ ፪ ስለሚመጣው ክህደት ተናግሯል። ምዕራፍ ፫ ለመንጌሉ ምክንያት ድል ማግኘት የነበረውን የጳውሎስ ጸሎትን የያዘ ነበር።

ወደ ቲቶ መልእክት። *ደግምም ቲቶ፤ የጳውሎስ መልእክቶች፤ ጳውሎስ ተመልከቱ*

ጳውሎስ ለጊዜ ከሮሜ እስር ቤት ወጥቶ እያለ፣ መልእክቱን በቀርጤስ ለነበርው ጢቶ ጻፈ። ደብዳቤው ስለቤተክርስቲያኗ ድርጅት እና በውስጧ ስላለው ቅጣቶች ስለነበሩት ጥያቄዎች መልስ የሚሰጥ ነበር።

ምዕራፍ ፩ የጳውሎስን ሰላምታ እና ኤጲስ ቆጶስ ለመሆን ምን አይነት ብቁነት እንደሚያስፈልግና መመሪያዎችን የያዘ ነበር። ምዕራፎ ፪–፫ አጠቃላይ ትምህርቶችን እና የቀርጤስ ቤተክርስቲያን የተለያዩ ቡድኖችን እንዴት መቋቋም እንደሚችል ለቲቶ የላከውን የግል መልዕክት የያዙ ናቸው። ጳውሎስ ቅዱሳንን ባለጌነትን እንዲያቆሙ፣ ራስን ተቆጣጣሪና ታማኝ፣ እናም መልካም ስራን የሚቀጥሉ እንዲሆኑ አበረታታ።

ወደ ኤፌሶን መልእክት። *ደግምም የጳውሎስ መልእክቶች፤ ጳውሎስ ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ በሐዋሪያ ጳውሎስ ለኤፌሶን ቅዱሳን የጻፈው መልእክት። መልእክቱ በጣም አስፈላጊ ነው፣ ምክንያቱም ጳውሎስ ስለኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማራቸውን ይዟል።

ምዕራፍ ፩ እንደ በፊቱ አይነት ሰላምታን ይዟል። ምዕራፍ ፪–፫ የቤተክርስቲያኗ አባላት በሚሆኑበት ጊዜ በሰዎች ላይ የሚመጣውን ቅያሬ ይገልጻል—ከቅዱሳን፣ ከአህዛባች እና ከአይሁድ ጋር በአንድ ቤተክርስቲያን በመተባበር ዜጋዎች ይሆናሉ። ምዕራፍ ፬–፮ የሐዋሪያትን እና የነቢያትን ሀላፊነቶች፣ ስለአንድነት አስፈላጊነት፣ እና የእግዚአብሔርን ሙሉ የጦር እቃ የመልበስ አስፈላጊነትን ይገልጻሉ።

ወደ ዕብራውያን መልእክት። *ደግምም የጳውሎስ መልእክቶች፤ ጳውሎስ ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያለ መፅሐፍ። ጳውሎስ ይህን ደብዳቤ የጻፈው አይሁድ የሆኑትን የቤተክርስቲያን አባላት አብዛኛዎቹ የሙሴ ህግ በክርስቶስ እንደተሟላ እና የክርስቶስ ታላቁ የወንጌል ህግ ይህን እንደተካ ለማሳመን ነበር። ከሶስተኛው ሚስዮኑ መጨረሻ ላይ (በ፶ ም.ዓ. አካባቢ) ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመለስ፣ ብዙዎቹ የቤተክርስቲያኗ አይሁድ አባሎች የሙሴን ህግ እያከበሩ እንዳሉ አገኛቸው (የሐዋ. ፳፩፡፣፳)። ይህም በኢየሩሳሌም የነበረው የቤተክርስቲያኗ ጉባኤ አንዳንድ የሙሴ ህግ ስነስርዓቶች ለአህዛብ ክርስቲያኖች አስፈላጊ እንዳልሆነ ከተወሰነ ከአስር አመት በኋላ ነበር። ጳውሎስ ከዚህ በኋላ በእራሳቸው ቅዱሣት መጻህፍት እና ግልፅ ምክንያት በመስጠት የሙሴን ህግ ከዚህ በኋላ ለምን መከተል እንደማያስፈልጋቸው ወደ ዕብራውያን እንደጻፈ ግልፅ ነው።

ምዕራፍ ፩ እና ፪ ኢየሱስ ከመላእክት በላይ ታላቅ እንደሆነ ይገልጻሉ። ምዕራፍ ፫–፮ ኢየሱስን ከሙሴና ከሙሴ ህግ ጋር ያነጻጽራሉ እናም እርሱ ከሁለቱም ታላቅ እንደሆነ ይመሰክራሉ። የመልከጼዴቅ ክህነት ከአሮናዊ ክህነት ታላቅ እንደሆነም ያስተምራሉ። ምዕራፍ ፯–፱ የሙሴአዊ ስነስርዓቶች ሰዎችን ለክርስቶስ አገልግሎት እንዴት እንደሚያዘጋጁና ክርስቶስ እንዴት የአዲሱ ቃል ኪዳን አማላጅ እንደሆነ ይገልጻሉ (አልማ ፴፯፡፣፴፯–፴፰፤ ት. እና ቃ. ፹፬፡፣፳፩–፳፬)። ምዕራፍ ፲ ለትጉነትና ታማኝነት የሚገፋፋ ነው። ምዕራፍ ፲፩ የእምነት ፅሁፍ ነው። ምዕራፍ ፲፪ ግሰጻን እና ሰላምታን ይሰጣል። ምዕራፍ ፲፫ ስለጋብቻ ክብር እን ስለታዛዥነት አስፈላጊነት ይናገራል።

ወደ ገላትያ መልእክት። *ደግምም የጳውሎስ መልእክቶች፤ ጳውሎስ ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያለ መፅሐፍ። በገላትያ

ውስጥ ለሚኖሩት ቅዱሳን ሐዋሪያው ጳውሎስ የጻፈው ደብዳቤ ነበር። የዚህ ደብዳቤ ጭብጥ መልእክት እውነተኛ ነጻነት ለመገኘት የሚቻለው በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በመኖር ነው የሚል ነበር። ቅዱሳን የሙሴን ህግ መከተል አለባቸው የሚሉት የአይሁዳ ክርስቲያን ትምህርቶችን ከወሰዱ፣ በክርስቶስ ያገኙትን ነጻነት ይገድባሉ ወይም ያጠፉሉ። መልእክቱ ውስጥ ጳውሎስ የሐዋሪያ ሀላፊነቱን አረጋገጠ፣ የጽድቅ በእምነት ትምህርትን ገለጸ፣ እናም የመንፈሳዊ ሀይማኖት ታላቅ ዋጋን አረጋገጠ።

በምዕራፍ ፩ እና ፪፣ ጳውሎስ በገላትያ መካከል ስላለው ክህደት በተቀበለው ዜና ሀዘኑን ገለጸ እናም በሐዋሪያት መካከል ስላለው ቦታ ገለጸ። ምዕራፍ ፫ እና ፬ የእምነትና የስራ ትምህርቶችን ይወያያሉ። ምዕራፍ ፭ እና ፮ የእምነት ትምህርት ውጤቶች ስብከትን የያዙ ናቸው።

ወደ ጢማቴዎች መልእክት። *ደግሞም የጳውሎስ መልእክቶች፤ ጢሞቴዎስ፤ ጳውሎስ ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሁለት መፅሐፎች። ሁለቱም በቅድሚያ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የጻፋቸው ደብዳቤዎች ነበሩ።

፩ ጢሞቴዎስ፣ ጳውሎስ የመጀመሪያውን መልእክት የጻፈው ለመጀመሪያ ጊዜ ከታሰረ በኋላ ነበር። ጢሞቴዎስን በኋላ እንደገና ለመመለስ እያሰበ፣ በኤፌሶን ትቶት ሄዶ ነበር (፩ ጢሞ. ፫፡፲፬)። ነገር ግን፣ ጳውሎስ የሚዘገይ እንደሆነ ስላሰበ፣ ምናልባት ከመቄዶንያ፣ ምክር ለመስጠት እና ሀላፊነቱን ለማሟላት ለማበረታታት ወደ ጢሞቴዎስ ጻፈ (፩ ጢሞ. ፩፡፣ ፫)።

ምዕራፍ ፩ የጳውሎስን ሰላምታ እና ደግሞም በቤተክርስቲያኗ ለመገኘት ስለጀመሩት የሞኝነት ግምቶች መመሪያ የሰጠበትን የያዘ ነበር። ምዕራፍ ፪–፫ ስለህዝባዊ አምልኮ እና ስለአገልጋዮች ጸባይ እና አሰራር መመሪያ የሚሰጡ ነበሩ። ምዕራፍ ፬–፭ የኋለኛው ቀን ክህደትን መግለጫ እና የሚመራቸውን እንዴት ለማገልገል እንደሚችል ለጢሞቴዎስ የተሰጠን መመሪያ የያዙ ነበሩ። ምዕራፍ ፮ ታማኝ ለመሆን እና የአለም ሀብቶችን እንዲያስወግዱ የሚያበረታታ ነበር።

፪ ጢሞቴዎስ፣ ጳውሎስ ሁለተኛውን ደብዳቤ የጻፈው በታሰረበት በሁለተኛ ጊዜ፣ እና በስማዕቱ ከትንሽ ጊዜ በፊት ነበር። ይህም የሐዋርያውን የመጨረሻ ቃላት የያዘ እና ሞትን እንዴት በአስደናቂ ጉብዝና እና እምነት እንደተቋቋመ የሚያሳይ ነው።

ምዕራፍ ፩ የጳውሎስን ሰላምታ እና ለ ጢሞቴዎስ የሰጠውን ሀላፊነት የያዘ ነበር። ምዕራፍ ፪–፫ የተለያዩ ማስጠንቀቂያዎች እና መመሪያዎች፣ ወደፊት የሚመጡትን አደጋዊች ለመቋቋም ሀላፊነት የሚሰጡ ነበሩ። ምዕራፍ ፬ የሚክዱትን ምን ለማድረግ እንደሚችሉ ምክር የሰጠውን የያዘ የጳውሎስ ጓደኞች የተላከውን መልእክት የያዘ ነበር።

ወደ ፊልሞና መልእክት። *ደግሞም የጳውሎስ መልእክቶች፤ ጳውሎስ ተመልከቱ*

በጳውሎስ ከተጻፈው ደብዳቤ የተወሰደ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያለ መፅሐፍ። ወደ ፊልሞን ሰዎች የላከው መልእክት ጌታውን ስለዘረፈው እና ወደ ሮሜ ስለሸሸው ባሪያ አናሲሞስ በሚመለከት ለፊልሞን የላከው የግል ደብዳቤ ነበር። ጳውሎስ በቄላስይስ ወደሚገኘው ጌታው የጳውሎስ ደብዳቤ ወደ ቄላስይስ ከወሰደለት ከቲኪቆስ ጋር መልሶ ላከው። ጳውሎስ አናሲሞስ ይቅርታ እንዲሰጠው እና እንደ ክርስቲያን ወንድም እንዲቀበለው ጠየቀ። ጳውሎስ ይህን ደብዳቤ የጻፈው ለመጀመሪያ ጊዜ በሮሜ እስር ቤት እያለ ነው።

ወደ ፊልጵስዮስ መልእክት። *ደግሞም የጳውሎስ መልእክቶች፤ ጳውሎስ ተመልከቱ*

ጳውሎስ በፊልጵስዮስ ውስጥ ላሉት ቅዱሳን ለመጀመሪያ ጊዜ በሮሜ ውስጥ በእስር ቤት እያለ የጻፈው ደብዳቤ ነበር። አሁን ይህም በአዲስ ኪዳን ውስጥ ወደ ኢልጵስዮስ መልእክት የሚባል መፅሐፍ ነው።

ምዕራፍ ፩ የጳውሎስን ሰላምታ እና ስለአንድነት፣ ትሁትነት፣ እና ስለመፅናት የሚሰጠው መመሪያን የያዘ ነው። ምዕራፍ ፪ ሁሉም ለክርስቶስ እንደሚሰግዱ እና እያንዳንዱ ሰው የእራሱን ደህንነት ለመፈጸም እንደሚገባቸው ትኩረት ይሰጣል። በምዕራፍ ፫ ውስጥ፣ ጳውሎስ ሁሉንም ነገሮች ለክርስቶስ መስዋዕት እንዳደረገ ይገልጻል። በምዕራፍ ፬ ውስጥ፣ ጳውሎስ የፊልጵስዮስ ቅዱሳንን ለእርዳታቸው ያመሰግናል።

ዊትመር፣ ዴቪድ

በዳግም በተመለሰችው ቤተክርስቲያን ውስጥ ከመጀመሪያ መሪዎች አንዱ እና ስለመፅሐፈ ሞርሞን መለኮታዊ መንጭ እና እውነትነት ምስክር ከሆኑት ሶስት ምስክሮች አንዱ (ት. እና ቃ. ፲፩፣ ፲፯–፲፰)። ጌታ ለእርሱ የግል መመሪያ በትምህርት እና ቃል ኪዳኖች ፲፩ እና ፴፡፩–፬ ውስጥ ሰጠው።

ዊትመር፣ ጆን

በዳግም በተመለሰችው ቤተክርስቲያን ውስጥ ከመጀመሪያ መሪዎች አንዱ እና ከስምንቱ የመፅሐፈ ሞርሞን ምስክሮች አንዱ። “የስምንቱ ምስክሮች ምስክርን” በመፅሐፈ ሞርሞን መግቢያ ገጾች ውስጥ ተመልከቱ። ወንጌልን ለመስበክ ተጠርቶ ነበር (ት. እና ቃ. ፴፡፩–፲፩)።

ዊትመር፣ ፒተር ዳግማዊ

በዳግም በተመለሰችው ቤተክርስቲያን ውስጥ ከመጀመሪያ መሪዎች አንዱ እና ከስምንቱ የመፅሐፈ ሞርሞን ምስክሮች አንዱ። “የስምንቱ ምስክሮች ምስክርን” በመፅሐፈ ሞርሞን መግቢያ ገጾች ውስጥ ተመልክቱ። ጌታ ለእርሱ የግል መመሪያ በትምህርት እና ቃል ኪዳኖች ፲፮ እና ፴፡፩–፳ ውስጥ ተሰጠው።

ዊትኒ፣ ኒውል ኬ

በዳግም በተመለሰችው ቤተክርስቲያን ውስጥ ከመጀመሪያ መሪዎች አንዱ። ኒውል ኬ ዊትኒ የከርትላንድ ኦሀዮ (ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ) ኤጲስ ቆጶስ ነበር እና በኋላም እንደ ቤተክርስቲያና ኤጲስ ቆጶስ አመራር አገለገለ (ት. እና ቃ. ፳፪፡፩–፳፣ ፲፱፣ ፲፲፯)።

ውህደት። የሚስጥር ስብሰባ *ተምልከቱ*

ውልያምስ፣ ፍሬድሪክ ጂ

በዳግም በተመለሰችው ቤተክርስቲያን ውስጥ እንደ ከፍተኛ የክህንነ ስልጣን አመራር አማካሪ ያገለገለ ከመጀመሪያ መሪዎች አንዱ (ት. እና ቃ. ፴፩፣ ፶፡፮፣ ፲፱፣ ፲፳፡፲)።

ውድሩፍ፣ ውልፈርድ። *ደግምም መግለጫ፤ አስተዳደሪያዊ አዋጅ ፩ ተመልከቱ*

በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ ወንጌሉ በዳግም ከተመለሰ በኋላ አራተኛው የቤተክርስቲያኗ ፕሬዘደንት የነበሩት። የተወለዱት በ፲፰፻፲፯ (እ.አ.አ.) ነበር እናም በ፲፰፻፲፯፳፰ (እ.አ.አ.) ሞቱ።

በአስራ ሁለቱ ሸንጎ ውስጥ ሀላፊነትን እንዲያሟሉ ተጠሩ፣ ት. እና ቃ. ፲፲፰፡፮። በዘመን ሙላት ለመምጣት ከተጠበቁት ምርጥ መንፈሶችም መካከል ነበሩ፣ ት. እና ቃ. ፲፭፰፡፱፲። በቤተክርስቲያን ውስጥ ከአንድ ሚስት በላይ ማግባትን እንዲቆም ራዕይን ተቀበሉ፣ አ.አ. ፩።

ውግዘት። *ደግምም አመጽ፤ ክህደት ተመልከቱ*

ማውገዝ ቤተክርስቲያኗ ከምትቀጣበት መንገድ በጣም ጥብቅ የሆነው ነው። የተወገዘ ሰው የቤተክርስቲያን አባል አይደለም። የቤተክርስቲያን ባለስልጣኖች የጌታ ትእዛዛትን በመቃረን ለመኖር የሚመርጠውን እና በዚህም በቤተክርስቲያኗ አባል ለመሆን ብቁነትን የሚያጣውን ሰው ያወግዛሉ።

የብዙዎች ልብ ጠጥሯል፣ ስማቸው ተደምስሷል፣ አልማ ፩፡፳፬ (አልማ ፮፡፫)። ንሰሃ ካልገባ፣ ከህዝቦቼ መካከል አይቆጠርም፣ ፫ ኔፊ ፲፰፡፴ (ሞዛያ ፳፯)።

የሚያመንዝር፣ እናም ንሰሃ የማይገባ፣ ወደ ውጭ ይጣላል፣ ት. እና ቃ. ፵፪፡፳፬። ኃጢያትን የሚሰራና ንስሃ የማይገባ ወደ ውጭ ይጣላል፣ ት. እና ቃ. ፵፪፡፳፰። አስፈላጊ የሆኑ ችግሮችን የማስተካከያ ስነስርዓቶች ተሰጥተዋል፣ ት. እና ቃ. ፲፪ (ት. እና ቃ. ፵፪፡፲–፲፫)። ኤጲስ ቆጶስ የእስራኤል ዳኛ እንዲሆን ተመድቧል፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፷፪። ጻድቅ ህብረተሰቦች ሁሉ አባሎቻቸው በሚረብሹበት ጊዜ ለመቅጣት መብት፣ ት. እና ቃ. ፲፴፬፡፲።

ዐይነ-እርግብ

በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ (፩) የታቦትን ወይም የቤተመቅደስን ክፍሎች የሚያለያይ መከፋፈያ፣ (፪) የእግዚአብሔር እና የሰው መለያየት ምልክት፣ (፫) ሰዎች ፈታቸውን ወይም ጭንቅላታቸውን ለመሸፈን የሚጠቀሙበት ጨረቅ ወይም (፬) የሰዎችን የቅድመ ምድር ህይወት ትዝታን የሚዘጋ በእግዚአብሔር የተሰጠ ዝንጉነት።

መጋረጃውም በቅድስቱና በቅድስተ ቅዱሳኑ መካከል መለያ ይሁናችሁ፣ ዘፀአ. ፳፮፡፴፫።

የቤተ መቅደስ *መጋረጃ* ከላይ እስከ ታች ከሁለት ተቀደደ፣ ማቴ. ፳፯፡፶፩ (ማር. ፲፭፡፴፰፣ ሉቃ. ፳፫፡፴፭)። ዛሬስ በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደ ምናይ ነን በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን፣ ፩ ቆሮ. ፲፫፡፲፪።

እርሱም ያለማመን ጥቁር *መጋረጃው* ከአዕምሮው እንደተወሰደ ያውቅ ነበር፣ **አልማ** ፲፱፡፯። የያሬድ ወንድም በ*መጋረጃው* ውስጥ ከመመልከት ሊጠበቅ አልቻለም፣ ኤተር ፫፡፲፱ (ኤተር ፲፪፡፲፱)።

መጋረጃውም ይገፈፋል እናም አይታችሁኝ፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፲ (ት. እና ቃ. ፴፳፡፳)። ቤተ መቅደሴን የሚሸፍነው *መጋረጃ* ይወልቃል፣ ት. እና ቃ. ፲፩፡፳፫። *መጋረጃው* ከአዕምሮዎቻችን ተወገደ፣ ት. እና ቃ. ፲፣፡፩።

የጭለማም *መጋረጃ* ምድርን ይሸፍናል፣ ሙሴ ፯፡፳፩።

ዑር

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የከለዳውያን ዑር የአብራም የመጀመሪያ ቤት ነበር (ዘፍጥ. ፲፩፡፳፯–፳፰፣ ፴፩፡፲ ፲፭፡፯፣ ነህ. ፱፡፯፣ አብር. ፪፡፩፣ ፱)።

ዔሳው። *ደግምም ያዕቆብ፣ የይስሐቅ ልጅ፣ ይስሐቅ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የይስሀቅ እና የርብቃ የመጀመሪያ ልጅ እና የያዕቆብ መንታ ወንድም። ከተወለዱበት ጊዜ ጀምሮ ሁለቱ ወንድሞች ይፎካከሩ ነበር (ዘፍጥ. ፳፭፡፲፱–፳፯)። የዔሳው ትውልዶች፣ ኤዶማውያን፣ እና የያዕቆብ ትውልዶች፣ እስራኤላውያን፣ የሚፎካከሩ ሀገሮች ሆኑ (ዘፍጥ. ፳፭፡፳፫)።

ዔድን

ዔሳው ብኵርናውንም ለያዕቆብ ሸጠ፣ ዘፍጥ. ፳፭፡፴፫ (ዕብ. ፲፪፡፲፮–፲፯)። ዔሳው ወላጆቹን በማሳዘን የኬጢ ሚስቶች አገባ፣ ዘፍጥ. ፳፮፡፴፬–፴፭። ያዕቆብ እና ዔሳው ታረቁ፣ ዘፍጥ. ፴፫።

ዔድን። *ደግሞም ሔዋን፣ አዳም ተመልከቱ*

የመጀመሪያ ወላጆቻችን፣ አዳምና ሔዋን፣ ቤት (ዘፍጥ. ፪፡፰–፲፡፳፬፣ ፴፡፲፯፣ ፪ ኔፊ ፪፡፲፱–፳፭፣ ሙሴ ፣–፴፣ አብር. ፭)፣ ይህም በስተምስራቅ ዔድን እንደገነት ተመድቦ ነበር። አዳምና ሔዋን የተከለከለውን ፍሬ ከበሉ በኋላና ሟች ከሆኑ በኋላ ከዔድን እንዲወጡ ተደረጉ (ሙሴ ፪፡፳፭–፳፱)። የኋለኛው ቀን ራዕይ የመፅሐፍ ቅዱስ የዔድን ገነት ታሪክን አረጋግጧል። ገነት ይገኝበት የነበረው አሁን የሰሜን አሜሪካ በሚባለው ክፍለ አህጉር ውስጥ እንደነበረ አስፈላጊ መረጃ ጨምሯል።

ዕብራይስጥ። *ደግሞም እስራኤል ተመልከቱ*

የእስራኤል ልጆች የሚናገሩት የሴም ቋንቋ።

ከባቢሎን ምርኮ እስከሚመለሱ ድረስ እስራኤል ዕብራይስጥ ቋንቋ ይናገሩ ነበር፣ በዚያም ጊዜ አራሚኛ የየቀኑ የንግግር ቋንቋ ሆነ። በኢየሱስ ዘመን፣ ዕብራይስጥ የተማሩት፣ የህግ፣ እና የሀይማኖት መፅሐፎች ቋንቋ ነበር።

ዕንባቆም

በይሁዳ ውስጥ ምናልባት በዮአኪን አገዛዝ ዘመን ስለህዝቡ ኃጢያተኛነት የተናገረ የብሉይ ኪዳን ነቢይ (በ፲፯ ም.ዓ. አካባቢ)።

ትንቢተ ዕንባቆም፣ ምዕራፍ ፩ በኤርምያስ ፲፪ እና በትምህርት እና ቃል ኪዳን ፻፳፩ ውስጥ እን ደሚገኙት አይነት በጌታ እና በነቢዩ መካከል የነበረ ውይይት ነው። በምዕራፍ ፪ ውስጥ ጌታ ዕንባቆምን ትዕግስተኛ እንዲሆን መከረው—ጻድቅ ሰው በእምነት ለመኖር ይማራል። ምዕራፍ ፣ የእግዚአብሔርን ፍትህ የተቀበለበትን የዕንባቆምን ጸሎት መዝግቧል።

ዕዝራ

አንዳንድ አይሁዶችን ከባቢሎን ምርኮ ወደ ኢየሩሳሌም ያመጣቸው የብሉይ ኪዳን ካህንና ጸሀፊ (ዕዝ. ፯–፲፣ ነህ. ፰፣ ፲፪)። በ፱፻፹፮ ም.ዓ. ከፋርስ ንጉስ አርጤክስስ ለመሄድ የሚፈልገውን ማንኛውንም የአይሁድ ስደተኛ ወደ ኢየሩሳሌም ለመውሰድ ፈቃድ አገኘ (ዕዝ. ፯፡፲፪–፳፭)።

ከዕዝራ ጊዜ በፊት፣ “ህግ” ተብለው የሚጠሩትን የተጻፉ ቅዱሣት መጻህፍትን በማንበብ ላይ ካህናት ሙሉ ስልጣን ነበራቸው። ዕዝራ ቅዱስ መጻህፍቱ ለሁሉም አይሁዶች ለመገኘት እንዲችሉ ረዳ። “የህጉ መፅሐፍ” መነበብ የአይሁዳ ሀገር ህይወት ዋና ክፍል ሆነ። ከዕዝራ ትምህርቶች ታላቁ ቢኖር የጌታን ህግ ለመፈለግ፣ ለማክበር፣ እና ለሌሎች ለማስተማር ልቡን ያዘጋጀበት የእራሱ ምሳሌ ነበር (ዕዝ. ፯፡፣)።

መፅሐፈ ዕዝራ፣ ምዕራፍ ፩–፯ ዕዝራ በኢየሩሳሌም ከመድረሱ ከስልሳ እስከ ሰማኒያ አመት በፊት የነበሩትን፣ በ፩፻፱፻፯ ም.ዓ. የቂሮስ አዋጅ እና በዘሩባቤል ስር የአይሁዳ መመለስ አይነት ድርጊ ቶችን ይገልጻሉ። ምዕራፍ ፯–፲ ዕዝራ ወደ ኢየሩሳሌም እንዴት እንደተመለሰ ያሳያሉ። እርሱ እና ከእርሱ ጋር የሚጓዙት ለጥበቃ ጾሙም ጸለዩም። በኢየሩሳሌም በዘሩባቤል ስር ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱና ከቃል ኪዳን ውጪ ሴቶችን ያገቡና በዚህም እራሳቸውን ያረከሱ ብዙ አይሁዶችን አገኙ። ዕዝራ ለእነርሱ ጸለየ እና ባለቤቶቻቸውን እንዲፈቱ በቃል ኪዳን ስር አደረጋቸው። የዕዝራ የኋለኛ ታሪክም በመፅሐፈ ነህምያ ውስጥ ይገኛል።

ዕጣ

የተለያዩ ምርጫዎችን የሚመረጥበት ወይም የሚወገድበት መንገድ፣ በብዙም ጊዜ የሚደረገው አንድ ወረቀትን ወይም እንጨትን ለብዙዎች መካ ከል በመምረጥ ነው። ይህም እጣ መጣል ይባላል።

ከሰቀሉትም በኋላ ልብሱን ዕጣ ጥለው ተካፈሉ፣ ማቴ. ፳፯፡፣፲፰ (መዝ. ፳፪፡፲፰ ማር. ፲፭፡፳፬፣ ሉቃ. ፳፫፡፴፬፣ ዮሐ. ፲፱፡፳፬)። ዕጣም ተጣጣሉላ ቸው፥ ዕጣውም ለማትያስ ወደቀ፣ የሐዋ. ፩፡፳፫–፳፮።

ማን ወደ ላባን ቤት መሄድ እንዳለበት ዕጣ ተጣ ጣልን፣ ፩ ኔፊ ፣፡፲፩።

ዘለአለማዊ ቃል ኪዳን

ዘለአለማዊ ቃል ኪዳን። ቃል ኪዳን፣ አዲስ እና የዘለአለም ቃል ኪዳን *ተመልከቱ*

ዘለአለማዊ አባት

ዘለአለማዊ አባት። እግዚአብሔር፣ አምላክ፣ የሰማይ አባት *ተመልከቱ*

ዘለዓለማዊነት

ዘለዓለማዊነት። ከፍተኛነት *ተመልከቱ*

ዘመን

ዘመን። *ደግሞም ክህነት፣ ወንጌል፣ የክህነት ቁልፎች፣ የወንጌል ዳግም መመለስ ተመልከቱ*

የወንጌል ዘመን ጌታ በምድር ላይ የቅዱስ ክህነት ቁልፍ ያለው አንድም የሚሆን ባለስልጣን በምድር ላይ የነበረበት ጊዜ ነው።

አዳም፣ ሔኖክ፣ ኖህ፣ አብርሐም፣ ሙሴ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ጆሴፍ ስሚዝ፣ እና ሌሎች አዲስ የወንጌል ዘመንን እያንዳንዳቸው ጀምረዋል። ጌታ ዘመንን ሲያደራጅ፣ የእዚያ ዘመን ህዝቦች በወደ ፊቱ ዘመን ለደህንነት አላማ እውቀት የሚመኩ እን ዳይሆኑ ወንጌሉን እንደ አዲስ ይገለጻል። በጆሴፍ

ስሚዝ የተጀመረው ዘመን “የዘመን ፍጻሜ” ተብሎ ይታወቃል።

የሰማይ አምላክ መንግሥት ያስነሣል፣ ዳን. ፪፡፵፬ (ት. እና ቃ. ፰፩)።

በመጨረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል፣ ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ፣ የሐዋ. ፪፡፲፯ (ኢዩ. ፪፡፳፰)። ገር ሁሉ እስከሚታደስበት ዘመን ድረስ ሰማይ ክርስቶስን ይቀበለው ዘንድ ይገባል፣ የሐዋ. ፫፡፳፩። በዘመን ፍጻሜ፣ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገሮች በክርስቶስ ይጠቀልላል፣ ኤፌ. ፩፡፣። ቤተክርስቲያኔን በእነርሱ መካከል እመሰርታ ለሁ፣ ፫ ኔፊ ፳፩፡፳፪።

ጌታ ለመጨረሻው ጊዜ የዘመነ ፍጻሜን ወን ጌልና የመንግስቱን ቁልፎች ሰጠ፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፲፫። የዘመን ቁልፎች በእጆቻችሁ ተሰጥተ ዋል፣ ት. እና ቃ. ፴፣፡፲፪–፲፯። የድሮ ዘመን ቁል ፎች በሙሉ በዘመን ፍጻሜ በዳግም ተመልሰዋል፣ ት. እና ቃ. ፴፯፳፡፲፳–፳፩።

ዘሩባቤል

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ ቂሮስ ለአይሁዶች ወደ ፍልስጥኤም እንዲመለሱ ፈቃድ ሲሰጣቸው፣ ዘሩባቤል እንደ አስተዳዳሪ ወይም እንደ አይሁዳ ልውል ቤት ወኪል ተመድቦ ነበር። የፋርሳዊው ስም ሰሳብሳር ነበር (ዕዝ. ፩፡፰)። የኢየሩሳሌም ቤተመ ቅደስን በመገንባትም ተሳታፊ ነበር (ዕዝ. ፫፡፪፣ ፳፣ ፭፡፪)።

ዘካሪያስ፡ ደግሞም መጥምቁ ዮሐንስ፤ ኤልሳቤጥ *ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ የመጥምቁ ዮሐንስ አባት። ዘካሪያስ የካህን ሀላፊነት ነበረው እናም በቤተመቅ ደስ ውስጥ አገለገለ።

ዘካሪያስ በቤተመቅደሱ እና በመሰዊያው መካከል ተገደለ፣ ማቴ. ፳፫፡፴፭ (ሉቃ. ፲፩፡፶፩)። መል ዓኩ ገብርኤል ዘካሪያስን እና ሚስቱ ኤልሳቤጥን ወንድ ልጅ እንደሚወልዱ ቃል ገባላቸው፣ ሉቃ. ፩፡፭–፳፭ (ት. እና ቃ. ፳፯፡፣)። ምላሱ ተፈታ፣ ሉቃ. ፩፡፶፱–፷፬።

ዘይት፡ *ደግሞም ለታመሙት አገልግሎት መስጠት፤ መቀባት፤ የወይራ ዛፍ ተመልከቱ*

በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ ዘይት ሲጠቀስ፣ ብዙ ጊዜ የወይራ ዛፍ ዘይት ማለት ነው። ከብሉይ ኪዳን ዘመናት ጀምሮ፣ የወይራ ዛፍ ዘይት ለቤተመቅደስ እና ለድንኳን ስርዓት፣ ፋኖስ ለማብራት፣ እና ለም ግብ የሚጠቀሙበት ነው። የወይራ ዘይት አንዳንዴ ለንጹህነት እና ለመንፈስ ቅዱስና ለእርሱ ተጽዕኖ ምልክት ነው (፩ ሳሙ. ፲፡፩፣ ፲፣ ፲፮፡፲፫፣ ኢሳ. ፷፩፡፩–፫)።

ካህኑም በእጁ ውስጥ ካለው ዘይት የሚነጻውን ሰው የቀኝ ጆሮውን ጫፍ ላይ ያስነካዋል፣ ዘሌዋ. ፲፬፡፳፭–፳፱። በሕዝቡ በእስራኤል ላይ ንጉሥ እንድትሆን እቀባህ ዘንድ እግዚአብሔር ላከኝ፣ ፪ ሳሙ. ፲፮፡፩። ዘይቱም ከባልቴቷ ማሰሮው አል ጎደለም፣ ፪ ነገሥ. ፲፣፡፣–፲፯። ጌታ ራሴን በዘይት ቀባህ፣ መዝ. ፳፫፡፩።

ብዙ ድውዮችንም ዘይት ቀቡ፣ ማር. ፮፡፲፫። ሽምግሌዎች እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት፣ ያዕ. ፭፡፲፫–፲፭።

መብራታችሁን አስተካክላችሁ ለኩሱ እና ዘይታ ችሁን ያዙ፣ ት. እና ቃ. ፴፫፡፲፣ (ማቴ. ፳፭፡፩–፲፫)።

ዚኖስ

ስለክርስቶስ ተልዕኮ የተነበየ በብሉይ ኪዳን ዘመን በመዕሐፈ ሞርሞን ውስጥ ብቻ የተጠቀሰ የእስራ ኤል ነቢይ።

ስለክርስቶስ መቀበር እና ስለሶስት ቀን ጭለማ ተነበየ፣ ፮ ኔፊ ፲፱፡፣፣ ፲፪። ስለእስራኤል መሰብ ሰብ ተነበየ፣ ፮ ኔፊ ፲፱፡፲፯። ያዕቆብ ከዚኖስ ስለለ ማው እና ስለዱር የወይራ ዛፍ ታሪክ ጠቀሰ፣ ያዕቆ. ፭። ያዕቆብ የዚኖስን ምሳሌ አብራራ፣ ያዕቆ. ፮፡፩–፣። ጸሎትን እና አምልኮን በሚመለከት አስተማረ፣ አልማ ፴፫፡፣–፲፩። ቤዛነት የሚመጣው በወልድ በኩል እንደሆነ አስተማረ፣ አልማ ፴፬፡፮። ለደ ፋር ምስክሩ ተገደለ፣ ሔሌ. ፭፡፲፱። ስለላማናው ያን ዳግም መመለስ ተመለሰ፣ ሔሌ. ፲፭፡፲፩። በክ ርስቶስ ሞት ስለሚመጣው ጥፋት መሰከረ፣ ፫ ኔፊ ፣፡፲፭–፲፯።

ዚኤዝሮም

በመዕሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ በአሞኒሀ ከተማ ውስጥ የነበረ ጠበቃ። አልማ እና አሙሌቅ በመንፈስ በኩል ዚኤዝሮም እንደዋሸ ለመመልከት ቻሉ። በኋ ላም ወደ ክርስቶስ ወንጌል ተቀየረ (አልማ ፲፩፡፳፩–፳፯፣ ፲፭፡፩–፲፪)።

ዛራሔምላ፡ *ደግሞም ሙሌቅ፤ አሞን፣ የዛራሔምላ ትውልድ ተመልከቱ*

በመዕሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ ዛራሔምላ (፩) የሙሌቅ ግዛትን የሚመራን ሰው፣ (፪) ከእርሱ ስም የተጠራ ከተማ፣ (፫) የዛራሔምላ ምድር፣ ወይም (፬) እርሱን የሚከተሉ ሰዎችን የሚጠቁም ነው።

ጌታ ኔፋውያንን ስለላከ ዛራሔምላ እጅግ ተደ ሰተ፣ ኦምኒ ፩፡፲፬። ዛራሔምላ የአባቶቹን ትው ልድ ሐረግ ሰጠ፣ ኦምኒ ፩፡፲፰። አሞን የዛራሔምላ ትውልድ ነበር፣ ሞዛያ ፯፡፫፣ ፲፫። ቤተክርስቲ ያኗ በዛራሔምላ ከተማ ተመሰረተች፣ አልማ ፩፡፪። ፃድቃን በሆኑት ምክንያት ነው ዛራሔምላ

የዳነችው፣ ሔሌ. ፲፫፡፲፪። በክርስቶስ ሞት ጊዜ የዛራሔምላ ከተማ ተቃጠለ፣ ፫ ኔፊ ፰፡፰፣ ፳፩።

ዛብሎን። *ደግሞም* እስራኤል፣ *ያዕቆብ፣ የይስሐቅ ልጅ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የያዕቆብ እና የልያ ወንድ ልጅ (ዘፍጥ. ፴፡፲፱–፳)።

የዛብሎን ጎሳ፣ ያዕቆብ የዛብሎን ጎሳን ባረከ (ዘፍጥ. ፵፱፡፲፫)። የዛብሎን ጎሳ ከዲቦራ እና ከባርቅ ጋር ከእስራኤል ጠላቶች ጋር ለመዋጋት ተባበረ (መሳ. ፬፡፭–፮፣ ፣)። እነርሱም ከጌዴዎን ጋር ተባብሮ ከምድያማውያን ጋር ተዋጋ (መሳ. ፮፡ ፡፲–፳)።

ዛካርያስ

በ፭፻፳ ም.ዓ. አካባቢ የተነበየ የብሉይ ኪዳን ነቢይ። ነቢዩ ሐጌ በኖረበት ጊዜ የሚኖር ነበር(ዕዝ. ፭፡፩፣ ፮፡፲፬)።

ትንቢተ ዛካርያስ፣ መፅሐፉ ስለክርስቶስ የም ድር አገልግሎት እና ስለዳግም ምፅዓቱ ስላለው ትንቢቶች የታወቀ ነው (ዘካ. ፱፡፱፣ ፲፩፡፲–፲፣ ፲፪፡፲፣ ፲፣ ፲፣ ፲፡፲)። ምዕራፍ ፩–፰ ስሌማዚአብሔር ህዝቦች ወደፊት ራዕዮችን የያዙ ነበሩ። ምዕራፍ ፱–፲፬ ስለመሲህ፣ ስለመጠረሻው ቀናት፣ ስለእስራ ኤል መሰብሰብ፣ ስለመጠረሻው ታላቅ ጦርነት፣ እና ስለዳግም ምፅዓት ራዕዮችን የያዙ ናቸው።

ዜኒፍ

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ ወደ ኔፊ ምድር የተመለሱትን ቡድኖች የመራ ሰው፣ የእነርሱ ንጉስ ሆነ እናም በጻድቅ መራቸው (ሞዛያ ፱–፣)።

ዜና ማዋእል

በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚገኙ ሁለት መጻህፍቶች። እነዚህም ከፍጥረት ጀምሮ አይሁድ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለሱ እስከታወጀበት ድረስ የነበሩትን ድርጊቶች አጭር ታሪክ ይዘረዝራሉ።

ዜና ማዋእል ቀዳማዊ፣ ምዕራፍ ፩–፱ ከአዳም እስከ ሳኦል የነበሩትን ትውልዶች ይዘረዝራሉ። ምዕራፍ ፣ የሳኦል ሞትን ይዘረዝራል። ምዕራፍ ፲፩–፳፱ የዳዊት ግዛት ጋር የተያያዙትን ድርጊቶች ይገልጻል። ምዕራፍ ፳፫–፳፯ ሰለሞን እንደነገሰና ሌዋውያን በስነስርዓት እንደተደራጁ ይገልጻሉ። ምዕራፍ ፳፰ ዳዊት ለሰሞንን ቤተመቅደስ እንዲ ገነባ እንዳዘዘው ይገልጻል። ምዕራፍ ፳፱ የዳዊት ሞትን ይመዘግባል።

ዜና ማዋእል ካልዕ፣ ምዕራፍ ፩–፱ ከሰለሞን ግዛት ጋር የተያያዙትን ድርጊቶች ይገልጻል። ምዕራፍ ፣–፲፪ አንድ የነበረው የእስራኤል መንግስት ወደ ሰሜንና ደቡብ ግዛት ስለተከፋፈለበት ስለሰለሞን ልጅ ሮብዓም ግዛት ይናገራሉ። ምዕራፍ ፲፫–፴፮ ናቡከደነፆር የአይሁድን መንግስት በምርኮ እስከ ሚይዝበት ድረስ የነበሩትን የተለያዩ ንጎሶች ይገ ልጻል። መፅሐፉም ቂሮስ በምርኮ የተያዙት የአይ ሁድ ልጆች ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለሱ በሚያ ውጅበት ይፈጸማል።

ዜኖቅ

በብሉይ ኪዳን ዘመን በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ ብቻ የተጠቀሰ የእስራኤል ነቢይ።

ስለክርስቶስ ሞት ተነበየ፣ ፩ ኔፊ ፲፱፡፣። ስለእግ ዚአብሔር ልጅ ተናገረ፣ **አልማ** ፴፫፡፲፩ (**አልማ** ፴፴፡፯)። ለእውነት ሰማዕት ነበር፣ **አልማ** ፴፫፡፲፯። ስለመሲሕ መምጻት ተነበየ፣ ሔሌ. ፰፡፳፰።

ዝሙት መፈጸም

ደግሞም ማመንዘር፣ ስሜታዊ፣ ስሜታዊነት፣ ንጹህነት ተመለከቱ

ባልተጋቡ ሰዎች ወከከል የሚፈጸም ህጋዊ ያል ሆነ ፍትወተ ስጋ ግንኙነት። በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ ይህም እንደ ክህደት ምሳሌ የሚጠቀሙበት አንዳንድ ጊዜዎች አሉ።

ከዝሙት የራቃችሁ ሁኑ፣ **የሐዋ.** ፲፭፡፳፱። ሰውነት ለጌታ እንጂ ለዝሙት አይደለም፣ ፩ ቆሮ. ፮፡፲፫–፲፰። ስለ ዝሙት ጠንቅ ለእያንዳንዱ ለራሱ ሚስት ትኑረው፣ ፩ ቆሮ. ፯፡፪–፫። ይህ የእግዚአ ብሔር ፈቃድ ነው፣ ከዝሙት እንድትርቁ፣ ፩ ተሰ. ፬፡፫።

ያዕቆብ ህዝቡን ከዝሙትና አስጠነቀቀ፣ ያዕቆ. ፫፡፲፪። በመግደላችሁ፣ እናም ዝሙት በመፈፀማ ችሁ እንዲሁም በክፋታችሁ ለዘለዓለማዊው ጥፋት በስላችኋል፣ ሔሌ. ፲፡፳፯።

ዝሙት ፈጻሚዎች የቤተክርስቲያኗ አባል ለመ ሆን ንስሀ መግባት አለባቸው፣ ት. እና ቃ. ፵፪፡፳–፳፯።

ዞራም፣ ዞራማውያን

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ ወደ ቃል ኪዳን ምድር ለመምጣት ከኔፊ እና ከሌሂ ጋር የተባበረ የላ ባን አገልጋይ (፩ ኔፊ ፬፡፴–፴፭)። በዞራም ታማ ኝነት ምክንያት፣ ሌሂ ከሌሂ ልጆች ጋር አብሮ ባረ ከው (፪ ኔፊ ፩፡፴–፴፪)። ትውልዶቹ ዞራማውያን ተብለው ይታወቁ ነበር (ያዕቆ. ፩፡፲፫)።

የህይወት እንጀራ

ደግሞም ቅዱስ ቁርባን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልከቱ

ኢየሱስ ክርስቶስ የህይወት እንጀራ ነው። የቅዱስ ቁርባን እንጀራ (ዳቦ) የክርስቶስን ሰውነት በምሳ ሌነት ይወክላል።

የህይወት እንጀራ እኔ ነኝ፣ ዮሐ. ፮፡፴፫–፴፭።

የህይወትን ዳቦና ውኃ ተመገቡ እናም ጠጡ፣ **አልማ** ፮፡፴፱። ዳቦንም የክርስቶስን ስጋ በማስታ ወስ፣ ፲ ኔፊ ፲፯፡፮–፯። ዳቦ የክርስቶስ ስጋ ምልክት ነው፣ ት. እና ቃ. ፳፡፴፣ ፫፲፯ (ሞሮኒ ፱)።

የህይወት ዛፍ። *ደግሞም ዔድን ተመልከቱ*

በዔድን ገነት እና በእግዚአብሔር ገነት ውስጥ የሚገኝ ዛፍ (ዘፍጥ. ፪፡፱፣ ራዕ. ፪፡፯)። በሌሂ ህልም ውስጥ የህይወት ዛፍ የእግዚአብሔርን ፍቅር የወ ከለ እናም ከእግዚአብሔር ስጦታዎች ሁሉ ታላቅ ነበር (፩ ኔፊ ፡፲፡፲፩–፲፭)። ኪሩቤልንና የምትገለባበጥ የነበልባል ሰይፍ ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውንም መንገድ ጠበቁ፣ ዘፍጥ. ፫፡፳፬ (አልማ ፣ ፴፪–፴፫)።

ዮሐንስ የሕይወት ዛፍ አየ የዛፉም ቅጠሎች ለሕ ዝብ መፈወሻ ነበሩ፣ ራዕ. ፳፪፡፪።

ሌሂ የህይወት ዛፍን አየ፣ ፩ ኔፊ ፡፲–፲፭። ኔፊ አባቱ ያየውን ዛፍ አየ፣ ፩ ኔፊ ፲፡፡–፱። የብረት በትር ወደ ህይወት ዛፍ ይመራል፣ ፩ ኔፊ ፲፡፡፡ (፩ ኔፊ ፲፡፡፡–፳፪)። ከህይወት ዛፍ የሚለያይ አሰ ቃቂ ገደል ነበር፣ ፩ ኔፊ ፲፡፡–፲፡፡ ፡፲፡። የተከለከ ለውም ፍሬ እንደ ህይወት ዛፍ ተቃራኒ መኖሩ አስ ፈላጊ ነበር፣ ፪ ኔፊ ፪፡፲–፲፡። ወደ ጌታ ኑ እናም ከህ ይወት ዛፍም ፍሬ ትካፈላላችሁ፣ **አልማ** ፮፡፴፪፣ ፡፡፪። የመጀመሪያ ወላጆቻችን የህይወት ዛፍን መመ ገብ ቢችሉ ኖሮ ለዘለዓለም ደስታ የሌላቸው በሆኑ ነበር፣ **አልማ** ፲፪፡፡፲፣ ቃሉን የማትንከባከቡት ከሆነ፣ ከህይወት ዛፍ ፍሬ በጭራሽ መቅጠፍ አት ችሉም፣ **አልማ** ፴፪፡፴። ጌታ በገነትም መካከል የሕይወትን ዛፍ ተከለ፣ **ሙሴ** ፫፡፱ (አብር. ፭፡፱)። ከህይወት ዛፍ በል ተው እስከዘለአለም እንዳይኖሩ ዘንድ እግዚአብሔር አዳምን ከኤደን አስወጣው፣ **ሙሴ** ፪፡፳፯–፴፩።

የህጻን ጥምቀት። *ደግሞም ልጅ፣ ልጆች፣ መልስ መስጠት፣ ሂሳብ፣ ተጠያቂነት፣ ሀላፊነት፣ ደህንነት—የልጆች ደህንነት፣ ጥምቀት፣ መጥመቅ—ጥምቀት ለህጻናት አይደለም ተመልከቱ*

ስምንት አመት ከሆነው ከተጠያቂነት እድሜ በታች የሆኑትን ህጻናትን እና ልጆችን አስፈላጊ ሳይሆን የመ ጥመቅ ልምድ። ጌታ የህጻን ጥምቀትን ኩነኔ ነው አለ (ሞሮኒ ፰፡፣ ፣–፲፩)። ልጆች የዋህ እና ኃጢያት የሌ ላቸው ናቸው። ተጠያቂ እስከሚሆኑ ድረስ ሰይ ጣን ልጆችን ለመፈተን ሀይል የለውም (ት. እና ቃ. ፳፱፡፡፣ ፡፲፭–፡፲፯) ስለዚህ ንስሀ መግባት ወይም መጠ መቅ አያስፈልጋቸውም። ልጆች በስምንት አመት ላይ ይጠመቁ (ት. እና ቃ. ፡፡፡፡፡–፡፡፭)።

የሌዋውያን ክህነት። *አሮናዊ ክህነት ተመልከቱ*

የልሳኖች ስጦታ። *ደግሞም ምላስ፣ የመንፈስ ስጦታዎች ተመልከቱ*

የተነሳሱ ሰዎች የማያውቁትን ቋንቋ ለመናገር፣ ለማስተዋል፣ እና ለመተርጎም የሚያስችላቸው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ። በልሳኖች ስጦታ እናም ናለን (እ.ኢ. ፩፡፣)።

በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ በሌላ ልሳ ኖች ይናገሩ ጀመር፣ **የሐዋ.** ፪፡፬። በልሳን የሚ ናገርስ ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አይናገርም፣ ፩ ቆሮ. ፲፬፡፩–፩፣ ፡፡፣–፡፡፡። በልሳኖች መናገር ለማያምኑ ምልክት ነው፣ ፩ ቆሮ. ፲፬፡፡፪–፡፡፡።

ከዚያም የእሳትና የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ይመ ጣል፣ እናም ከዚያ በኋላ በመላዕክት ልሳን መናገር ትችላላችሁ፣ ፪ ኔፊ ፴፩፡፣ ፣–፣፬። አማሌቂ ሁሉም ሰዎች በልሳኖች መናገርን እንዲያምኑ አበረታታ፣ **ኦምኒ** ፩፡፡፡፩።

ለአንዳንዶቹ በልሳን መናገር ተሰጥቷቸዋል፣ ለሌላም በልሳኖች የተነገረውን መተርጎም ተሰጥቷ ቸዋል፣ ት. እና ቃ. ፴፯፡፡፩–፡፡፩ (፩ ቆሮ. ፲፪፡፣ ፣፡ ሞሮኒ ፣፡ ፡፡ ፣፩–፣፯)። የልሳኖች ስጦታ በህዝቦችህ ላይ ይፍሰስ፣ ት. እና ቃ. ፣፬፡ ፴፯፡፡፯።

የልብርቲ እስር ቤት፣ ምዙሪ (ዩ.ኤስ.ኤ.)። *ደግሞም ስሚዝ፣ ጆሴፍ ዳግማዊ ተመልከቱ*

ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ እና ሌሎች ፍትህዊ ባል ሆነ ጉዳይ ከህዳር ፣፡፡፣፴ (እ.አ.አ.) እስከ ሚያ ዝያ ፣፡፡፣፴ (እ.አ.አ.) ድረስ የታሰሩበት ትንሽ እስር ቤት። በእነዚህ አስቸጋሪ ጉዳዮች ላይ እያለ፣ ጆሴፍ አንዳንድ ራዕዮችን ተቀበለ፣ ትንቢቶችን ሰጠ፣ እናም ለቅዱሳን አስፈላጊ የሆነ ደብዳቤ እን ዲያነብ ተነሳሳ፣ ከዚህም የተወሰደ ምንባብ በት ምህርት እና ቃል ኪዳኖች ፣፡፡፩–፣፡፣ ውስጥ ይገ ኛሉ።

የልጆች ደህንነት። *ልጅ፣ ልጆች፣ ደህንነት—የልጆች ደህንነት ተመልከቱ*

የሐዋርያት ስራ። *ደግሞም ሉቃስ ተመልከቱ*

ለቴዎፍሎስ ሉቃስ የጻፈው ከሁለት ክፍል ስራ ይህ መፅሐፍ ሁለተኛው ነው። የመጀመሪያው ክፍል የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ቅዱስ ሉቃስ እንደጻፈው ተብሎ ይታወቃል። ምዕራፍ ፩–፣፪ ከአ ዳኝ ሞት እና ትንሳኤ ወዲያው በጴጥሮስ አመራር በኩል የነበሩትን የአስራ ሁለት ሐዋሪያት አንዳንድ ታላቅ የሚስዮን ስራዎችን ይመዘግባል። ምዕራፍ ፣፣–፡፡ የሐዋሪያው ጳውሎስን አንዳንድ ጉዞዎች እና የሚስዮን ስራዎችን ይዘረዝራል።

የሔለማን ልጆች። *ደግሞም ሔለማን፣ የአልማ ልጅ፣ አንቲ-ኔፊ-ሌሂ ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ በሔለማን ሀላፊ

ነት ስር ጀግናዎች የሆኑ አሞናዊያን ተብለው የሚ ታወቁት የተቀየሩት ላማናውያን ልጆች (አልማ ፱፫፡፲፯–፳፪)።

ሔሌማን ልጆች ተብለው ለመጠራት ብቁ እን ደሆኑ አሰበባቸው፣ **አልማ** ፶፯፡፲። እናቶቻቸው ጌታ እንደሚያድናቸው ጥርጣሬ እንዳይኖራቸው አስተምረዋቸዋል፣ **አልማ** ፶፯፡፳፯። ላማናውያ ንን አሸነፉ እናም በእምነታቸው ምክንያት ተጠብ ቀው ማንኛቸውም አልተገደሉም፣ **አልማ** ፶፯፡፱–፳፩፣ ፶፯፣ ፶፯፡፳፯።

የሕይወት መፅሐፍ። *ደግምም የመታሰቢያ መፅሐፍ ተመልከቱ*

በአንድ በኩል የህይወት መፅሐፍ የሰው ሀሳቦች እና ስራዎች ሙሉነት፣ የህይወቱ መዝገብ ነው። ነገር ግን ቅዱሣት መጻህፍት ከስሞቻቸው እና ከጻ ድቅ ድርጊቶቻቸው በተጨማሪ ስለታማኝ የሰማይ መዝገብ እንደሚጠበቅም ይጠቁማሉ።

የበደለኝን እርሱን ከመጽሐፌ እደመስሰዋለሁ፣ **ዘፀአ.** ፴፪፡፴፣፴፫።

ድል የነሣው. . . ስሙንም ከሕይወት መጽሐፍ አልደመስስም፣ **ራዕ.** ፫፡፭። ሌላ መጽሐፍም ተከ ፈተ እርሱም የሕይወት መጽሐፍ ነው፣ **ራዕ.** ፳፡፲፪ (ት. እና ቃ. ፲፳፳፡፭–፯)።

የጻድቃን ስሞች በሕይወት መፅሐፍ ውስጥ ይጻፋሉ፣ **አልማ** ፭፡፶፰።

በጸሎቶቻችሁ ተቀደሱት ስሞች መፅሀፍ ውስጥ ተመዝግበዋል፣ **ት. እና ቃ.** ፲፳፡፪።

የመለየት ስጦታ። *ደግምም የመንፈስ ስጦታዎች ተመልከቱ*

ማስተዋል ወይም አንድ ነገርን በመንፈስ ሀይል ማወቅ። የመለየት ስጦታ ከመንፈስ ስጦታዎች አንዱ ነው። ይህም የሰዎችን እውነተኛ ጸባይ እና በመን ፈስ መታየትን ምንጭና ትርጉምን ለይቶ የማወቅን ችሎታ ይጨምራል።

ሰው ፊትን ያያል፥ እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል፣ **፩ ሳሙ.** ፲፮፡፯። ክፉውን መልካም መል ካሙን ክፉ ለሚሉ ወዮላቸው፣ **ኢሳ.** ፭፡፳ (፪ ኔፊ ፲፭፡፳)።

የእግዚአብሔር ነገር በመንፈስ የሚመረመር ነው፣ **፩ ቆሮ.** ፪፡፲፬። ለአንዱም መናፍስትን የመ ለየት ስጦታ ተሰጥቷል፣ **፩ ቆሮ.** ፲፪፡፲።

አሞን ሀሳቡን ለመረዳት ችሏል፣ **አልማ** ፲፰፡፲፰። ድምፁ አነስተኛ ቢሆንም እንኳን የሰ ሙት ውስጣቸውን ሰንጥቆ ገብቶ፣ ፫ **ኔፊ** ፲፭፡፫።

እንዳትታለሉ፣ ከሁሉም የሚበልጡትን ስጦታ ዎች ፈልጉ፣ **ት. እና ቃ.** ፵፯፡፰፣ ፳፫።የቤተክ ርቲያና መሪዎች የመንፈስ ስጦታዎችን ለይተው እንዲያውቁ ተሰጥቷቸዋል፣ **ት. እና ቃ.** ፵፯፡፰፣ ብሩህ የሆነ ሰውነትም ሁሉንም ነገሮች ይረዳል፣ **ት. እና ቃ.** ፲፰፡፳፯፡፳፯።

ሙሴ ምድርን አየ፣ እና በእግዚአብሔር መንፈስ ለይቶ አወቀ፣ **ሙሴ** ፩፡፳፯፡፳፯።

የመላእክት አለቃ። *ደግምም ሚካኤል፣ አዳም ተመልከቱ*

ሚካኤል፣ ወይም አዳም፣ የመላእክት አለቃ ወይም የመላእክት መሪ ነው።

ጌታ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በመለከት ከሰ ማይ ይወርዳል፣ **፩ ተሰ.** ፬፡፲፮። ሚካኤል የመላእ ክት አለቃ ነው፣ ይሁዳ ፩፡፱ (ት. እና ቃ. ፳፱፡፳፯፣ ፲፰፡፲፪፣ ፲፳፳፡፳–፳፩)።

የመልከ ጼዴቅ ክህነት። *ደግምም መልከ ጼዴቅ፣ ሽማግሌ፣ ክህነት ተመልከቱ*

የመልከ ጼዴቅ ክህነት ከፍተኛው ወይም ታላቁ ክህነት ነው፤ የመልከ ጼዴቅ ክህነት የቤተክርስቲያና መንፈሳዊ በረከቶች ቁልፎችም ያለው ነው። በከፍ ተኛው ክህነት ስነስርዓቶች በኩል የአምላክነት ሀይል በሰው የሚገለፅበት ነው (ት. እና ቃ. ፲፱፡፣ ፲፳–፳፭፣ ፲፯፡፣ ፲፳–፳፩)።

እግዚአብሔር ይህን ከፍተኛ ክህነት ለአዳም ገለጸ። በሁሉም ዘመናት የአባቶች አለቃዎችና ነቢ ያት ይህ ስልጣን ነበራቸው (ት. እና ቃ. ፲፱፡፣ ፭–፲፯)። በመጀመሪያ ይህም እንደ እግዚአብሔር ልጅ ስርዓት ቅዱስ ክህነት ተብሎ ይጠራ ነበር። ይህም በኋላ እንደ መልከ ጼዴቅ ክህነት ታወቀ (ት. እና ቃ. ፲፯፡፪–፱)።

የእስራኤል ልጆች ለመልከ ጼዴቅ ክህነት መብ ቶችና ቃል ኪዳኖች ብቁ ባልሆኑበት ጊዜ፣ ጌታ ከፍተኛውን ህግ ወሰደ እናም ዳግማዊን ክህነትና ዳግማዊን ህግ ሰጣቸው (ት. እና ቃ. ፲፱፡፳፯–፳፯)። እነዚህም የአሮናዊ ክህነትና የሙሴ ህግጋት ተብለው ይጠሩ ነበር። ኢየሱስ ወደ ምድር ሲመጣ፣ የመልከ ጼዴቅ ክህነትን ለአይሁዶች ደግሞም መለሰ እናም በመካከላቸውም ቤተክርስቲያኗን እንደገና መገን ባት ጀመረ። ነገር ግን፣ ክህነት እና ቤተክርስቲያኗ በክህደት ምክንያት እንደገና ጠፉ። በኋላም እነዚህ በጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ በኩል በዳግም ተመለሱ (ት. እና ቃ. ፳፯፡፲፪–፲፫፣ ፲፳፳፡፳፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡ ፳፫)።

በመልከ ጼዴቅ ክህነት ውስጥ የሽማግሌዎች፣ የሊቀ ካህናት፣ የፓትሪያርክ፣ የሰባዎች፣ እና የሐ ዋርያ ሀላፊነቶች ይገኛሉ (ት. እና ቃ. ፲፯)። የመልከ ጼዴቅ ክህነት ሁልጊዜም በምድር ላይ ያለው የእግ ዚአብሔር መንግስት ክፍል ይሆናል።

የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ፕሬዘደንት የከፍተኛው ወይም የመልከ ጼዴቅ ክህነት ፕሬዘደንት ነው፣ እናም በምድር ላይ ያለችው የእግዚአብሔር መንግስትን በሚመለከት

ሁሉንም ቁልፎች የያዘ ነው። የፕሬዘደንትነት ጥሪ የሚያዘው በአንድ ጊዜ በአንድ ሰው ብቻ ነው፣ እና በምድር ላይ የክህነት ቁልፎችን በሙሉ ለመጠቀም ስልጣን ያለው እርሱም ብቻ ነው (ት. እና ቃ. ፻፯፥፳፬–፳፯፤ ፻፴፪፥፯)።

ክርስቶስ እንደ መልከ ጼዴቅ ሥርዓት ለዘላለም ካህን ይሆናል፣ መዝ. ፻፲፥፬ (ዕብ. ፭፥፮፤ ፲፤ ፯፥፲፩)።

የመልከ ጼዴቅ ክህነት ወንጌሉን ያስተዳድራል፣ ዕብ. ፯ (ት. እና ቃ. ፹፬፥፲፰–፳፭)።

መልከ ጼዴቅ ታላቅ እምነትን ተለማመደ፣ የሊቀ ካህንነት ሀላፊነትን ተቀበለ፣ አልማ ፲፫፥፲፰።

የመልከ ጼዴቅ ክህነት ለጆሴፍ ስሚዝ እና ለኦሊቨር ካውደሪ ተሰጠ፣ ት. እና ቃ. ፳፯፥፲፪–፲፫ (ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፸፪)። ይህ ክህነት የሚቀበለው በመሀላና በቃል ኪዳን ነው፣ ት. እና ቃ. ፹፬፥፴፫–፵፪። ሁለት ክፍሎች ወይም ዋና ክፍሎች አሉ፣ የመልከ ጼዴቅ እና አሮናዊ ክህነት፣ ት. እና ቃ. ፻፯፥፮። የመልከ ጼዴቅ ክህነት መንፈሳዊ በረከቶችን በሙሉ ለማስተዳደር መብቶች አለው፣ ት. እና ቃ. ፻፯፥፰–፲፰። ሙሴ፣ ኢልያ፣ እና ኤልያስ ለጆሴፍ ስሚዝ እና ለኦሊቨር ካውደሪ የክህነት ቁልፎችን ሰጧቸው፣ ት. እና ቃ. ፻፲፥፲፩–፲፮። ለእናንተ ለክህነት ስልጣኔ አባል የሆኑትን ባለስልጣኖች፣ የእዚያን ቁልፎች እንዲይዙ አሁን እሰጣችኋለሁ፣ ት. እና ቃ. ፻፳፬፥፻፳፫።

የመመርመር ስጦታ። *የመለየት ስጦታ ተመልከቱ*

የመታሰቢያ መፅሐፍ። *ደግሞም የሕይወት መፅሐፍ፤ የትውልድ ሐረግ ተመልከቱ*

በአዳም የተጀመረ በውስጡ የትውልዱ ስራዎች የተመዘገቡበት መፅሐፍ፤ ደግሞም ከእዚያ ጊዜ ጀምሮ በነቢያት እና በታማኝ አባላት የተጠበቁ እንደዚህ አይነት መዝገቦች። አዳም እና ልጆቹ በመነሳሻ መንፈስ የጻፉበት የመታሰቢያ መፅሐፍ፣ እና የትውልድ ሐረግን የያዘ የትውልድ መፅሐፍን ጠበቁ (ሙሴ ፮፥፭፣ ፰)። እንደዚህ አይነት መዝገቦች በመጨረሻ የሚፈረድብንን የመወሰን ክፍል ይኖራቸው ይሆናል።

የመታሰቢያ መጽሐፍ ተፅፎ ነበር፣ ሚል. ፫፥፲፮–፲፰ (፫ ኔፊ ፳፬፥፲፮–፲፰)።

በመታሰቢያ መጽሐፍ ውስጥ ተፅፈው የማይገኙት ሁሉ በእዚያ ቀን ምንም ውርስ አያገኙም፣ ት. እና ቃ. ፹፭፥፱። ሙታንም በመጻሕፍት ተጽፎ እንደ ነበረ እንደ ሥራቸው መጠን ተፈረደባቸው፣ ት. እና ቃ. ፻፳፰፥፯። የሙታናችንን መዝገቦች የያዘን መፅሀፍ እናቅርብ፣ ት. እና ቃ. ፻፳፰፥፳፬።

የመታሰቢያ መጻህፍቶችም ተጠበቁ፣ ሙሴ ፮፥፭–፰። የመታሰቢያ መጻህፍቶች አሉን፣ ሙሴ ፮፥፵፮። አብርሐም ለትውልዶቹ መዝገብ ለመጻፍ ጣረ፣ አብር. ፩፥፴፩።

የመቶ አለቃ

በሮሜ ጦር ሰራዎት ውስጥ ከሀምሳ እስከ አንድ መቶ የሆኑ የሰዎች ቡድኖችን የሚያዝ ባለስልጣን። እንደዚህ አይነት ቡድን የሮሜ የክፍለ ጦር አንድ አስራስድስተኛ ክፍል ነበር። (ደግሞም ማቴ. ፰፥፭፤ ሉቃ. ፳፫፥፵፯፤ ስራዎች ፲፥፩–፰ ተመልከቱ።)

የመንፈስ ስጦታዎች። *ደግሞም ስጦታ ተመልከቱ*

ብቁ ለሆኑ ግለሰቦች ለእራሳቸው ጥቅምና ሌሎችን ለመባረክ እንዲጠቀሙበት፣ ጌታ የሚሰጠው ልዩ መንፈሳዊ በረከቶች። ለመንፈስ ስጦታዎች ልዩ መግለጫ ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች ፵፮፥፲፩–፴፫፤ ፩ ቆሮ. ፲፪፥፩–፲፪፤ ሞሮኒ ፲፥፰–፲፰ አጥኑ።

የሚበልጠውን የጸጋ ስጦታ በብርቱ ፈልጉ፣ ፩ ቆሮ. ፲፪፥፴፩ (፩ ቆሮ. ፲፬፥፩)።

ኔፋውያን ብዙ የመንፈስ ስጦታዎች ተሰጥቷቸዋል፣ አልማ ፱፥፳፩። ጌታ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አይሰራም ለሚል ወዮለት፣ ፫ ኔፊ ፳፱፥፮። እግዚአብሔር ለታማኝ ስጦዎችን ይሰጣል፣ ሞር. ፱፥፯። ስጦታዎች በክርስቶስ መንፈስ ይሰጣሉ፣ ሞሮኒ ፲፥፲፯።

፲፩ ብዙ ስጦታዎች ስላሉ፣ እያንዳንዱም ሰው አንድ ስጦታ በእግዚአብሔር መንፈስ ተስጥቶታል፣ ት. እና ቃ. ፵፮፥፲፩። የቤተክርቲያኗ መሪዎች ስጦታዎችን ለይተው እንዲያውቁ ተሰጥቷቸዋል፣ ት. እና ቃ. ፵፮፥፳፯። የቤተክርስቲያኗ ፕሬዘደንት እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያኗ መሪ የሚሰጣቸው ስጦታዎች በሙሉ አሉት፣ ት. እና ቃ. ፻፯፥፺፩–፺፪።

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ። *ደግሞም መንፈስ ቅዱስ፤ ስጦታ፤ እግዚአብሔር፣ አምላክ፤ የመንፈስ ስጦታዎች ተመልከቱ*

የመንፈስ ቅዱስን ቋሚ ተፅዕኖ ማግኘት ብቁ የሆነ የእያንዳንዱ የተጠመቀ የቤተክርስቲያኗ አባል መብት ነው። ወደ እውነተኛው የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ሰው ከተጠመቀ በኋላ፣ ትክክለኛው ስልጣን ባለው ሰው እጆች በመጫን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ይቀበላል(የሐዋ. ፰፥፲፪–፳፭፤ ሞሮኒ ፪፤ ት. እና ቃ. ፴፱፥፳፫)። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን መቀበል እንደ እሳት ጥምቀት ነው ይባላል (ማቴ. ፫፥፲፩፤ ት. እና ቃ. ፲፱፥፴፩)።

ሰዎች ንስሐ እንዲገቡ፣ እንዲጠመቁ፣ እና የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ እንዲቀበሉ ታዝዘዋል፣ የሐዋ. ፪፥፴፰። ጴጥሮስ እና ዮሐንስ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን እጆችን በመጫን ሰጡ፣ የሐዋ.

፰፥፲፬–፳፪። መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው እጆችን በመጫን ነው፣ የሐዋ. ፲፱፥፪–፮።
የኃጢአታችሁ ስርየት የሚመጣው በእሳትና በመንፈስ ቅዱስ ነው፣ ፪ ኔፊ ፴፩፥፲፯።
እጆችን በመጫን የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ስለ መስጠት እናምናለን፣ እ.አ. ፩፥፬።

የመንፈስ አለም። *ሲኦል፤ ቅድመ ምድራዊ ህይወት፤ ገነት ተመልከቱ*

የመንፈስ እስር ቤት። *ሲኦል ተመልከቱ*

የመንፈስ ፍጥረት። *ደግሞም መፍጠር፣ ፍጥረት፤ ሰው፣ ሰዎች ተመልከቱ*

ጌታ ሁሉንም ነገሮች በፍጥረታዊ አካል ከመ ፈጠራቸው በፊት በመንፈሳዊ አካል ተፈጥረው ነበር (ሙሴ ፫፥፭)።

ጌታ እያንዳንዱን ተክል በምድር ከመኖሩ በፊት ፈጥሮት ነበር፣ ዘፍጥ. ፪፥፬–፮ (አብር. ፭፥፭)።
ሁሉንም ነገሮች በመንፈሴ ኃይል መጀምሪያ ስጋዊ ሁልተኛ መንፈሳዊ የሆኑትን ፈጥሬአቸዋ ለሁ፣ ት. እና ቃ. ፳፱፥፴፩–፴፪። መንፈሳዊ ነገሩ ጊዜአዊ በሆነው ምስል ነው፣ ት. እና ቃ. ፸፯፥፪።
እኔ አለምንና ስጋ ከማግኘታቸው በፊት ሰዎችን የፈጠርኩኝ ነኝ፣ ሙሴ ፮፥፶፩።

የመጀመሪያው ራዕይ። *ደግሞም ስሚዝ፣ ጆሴፍ ዳግማዊ፤ የወንጌል ዳግም መመለስ ተመልከቱ*

እግዚአብሔር አብ እና ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በጥሻ ውስጥ የታዩበት።
በጸደይ ፲፰፻፳ (እ.አ.አ.) ውስጥ፣ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ አስራ አምስት አመቱ ነበር። በፓልማይራ፣ ኒው ዮርክ ከተማ፣ ውስጥ ከቤተሰቡ ጋር ይኖር ነበር። ከቤተሰቡ ቤት በስተምዕራብ በኩል የትትልቅ ዛፎች ጥሻ ነበር። ጆሴፍ ወደዚህ ቦታ የትኛው ቤተ ክርስቲያን ትክክል እንደሆነ ለእግዚአብሔር ለመጸ ለይ ሄደ። መፅሐፈ ሞርሞንን እያነበበ እያለ መልሱን ከእግዚአብሔር መፈለግ እንዳለበት ተነሳስቶ ነበር (ያዕ. ፩፥፭–፮)። ለጸሎቱ መልስ፣ አብና ወልድ ለእ ርሱ ታዩት እናም በእዚያ ጊዜ በምድር ላይ የነበሩ ትን ማንኛውንም ቤተክርስቲያናት አባል እንዳይ ሆን ነገሩት፣ ሁሉም የተሳሳቱ ነበሩና (ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፲፭–፳)። ይህም ቅዱስ አጋጣሚ የወንጌሉን እና የክርስቶስ እውነተኛ ቤተክርስቲያን ዳግም መመለስ ያመጣ የተከታተሉ ድርጊቶችን ጀመረ።

የመጀመሪያው ፍሬዎች

በዘመን የሚሰበሰብ የመጀመሪያው አዝመራ። በብሉይ ኪዳን ዘመናት፣ እነዚህ ለጌታ ቀርበው ነበር (ዘሌዋ. ፳፫፥፱–፳)። ኢየሱስ ክርስቶስ በመጀመሪያ ከሞት የተነሳ ስለሆነ ለእግዚአብሔር የመጀመሪያው አዝመራ ነው (፩ ቆሮ. ፲፭፥፳፣ ፳፫፤ ፪ ኔፊ ፪፥፱)። ወንጌልን የተቀበሉ እና እስከ መጨረሻ በታማኝነት የጸኑ፣ የእግዚአብሔር ስለሆኑ፣ በምሳሌነት የመጀ መሪያ ፍሬዎች ናቸው።

በጉ ወደሚሄድበት የሚከተሉት ለእግዚአብሔር በኵራት ናቸው፣ ራዕ. ፲፬፥፬።
መጀምሪያ ከእርሱ ጋር የሚወርዱት፣ የመጀ መሪያ ፍሬዎች ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፹፰፥፺፰።

የመጨረሻ ቀናት፣ የኋለኛው ቀናት። *ደግሞም የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት፤ የጊዜዎች ምልክቶች ተመልከቱ*

አሁን የምንኖርባት ዘመን። ከጌታ ዳግም ምፅዓት በፊት ያሉ ቀናት (ዘመን)።

በኋለኛው ዘመን የሚያገኛችሁን እነግራችኋ ለሁ፣ ዘፍጥ. ፵፱፥፩። የሚቤዠኝ በመጨረሻም ዘመን በምድር ላይ ይቆማል፣ ኢዮብ ፲፱፥፳፭። በዘመኑም ፍጻሜ የእግዚአብሔር ቤት ይመሰረ ታል፣ ኢሳ. ፪፥፪።
በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን ይመ ጣል፣ ፪ ጢሞ. ፫፥፩–፯። በመጨረሻው ቀን የሚያ ሾፉት ዳግም ምፅዓትን ይክዳሉ፣ ፪ ጴጥ. ፫፥፫–፯።
እኔ የመጨረሻውን ቀን በተመለከተ እተነብይላ ችኋለሁ፣ ፪ ኔፊ ፳፮፥፲፬–፴።
በመጨረሻ ቀናትም በዚህ፣ እንዲሁም በኋለ ኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስ ቲያን፣ ስም ነው ቤተክርስቲያኔ የምትጠራው፣ ት. እና ቃ. ፻፲፭፥፬።
ክርስቶስ በመጨረሻው ቀናት፣ ይመጣል፣ ሙሴ ፯፥፷።

የመጨረሻው እራት። *ደግሞም ቅዱስ ቁርባን፤ ፋሲካ ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን መሰረት፣ ኢየሱስ ከመታሰሩና ከመሰቀሉ በፊት የበላው የመጨረሻ ምግብ (ሉቃ. ፳፪፥፲፬–፲፰)። እርሱ እና አስራ ሁለት ሐዋሪያቱ ይህን ምግብ በፋሲካ በሉት (ማቴ. ፳፮፥፲፯–፴፤ ማር. ፲፬፥፲፪–፲፰፤ ሉቃ. ፳፪፥፯–፲፫)።

አዳኝ እንጀራን እና ወይንን ባረከ እናም ለሐዋ ሪያት ሰጠ፣ ማቴ. ፳፮፥፳፮–፳፱ (ማር. ፲፬፥፳፪–፳፭፣ ሉቃ. ፳፪፥፯–፳)። ኢየሱስ የሐዋርያትን እግር አጠበ፣ ዮሐ. ፲፫። ይሁዳ ኢየሱስን የሚክድ እንደሆነ ተነገረ፣ ዮሐ. ፲፫፥፳፩–፳፮ (ማቴ. ፳፮፥፳–፳፭)።

የመፅሐፈ ሞርሞን ምስክሮች። *ደግሞም መፅሐፈ ሞርሞን፤ ምስክር ተመልከቱ*

ጌታ ከነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በተጨማሪ ሌሎችን ስለመፅሐፈ ሞርሞን መለኮታዊነት ምስክር እን ዲሰጡ አዘዘ (ት. እና ቃ. ፲፯፤ ፻፳፰፥፳)። የእነዚ

ህን ምስክሮች ቃላት በመፅሐፈ ሞርሞን መጀምሪያ ገጾች “በመግቢያው” ውስጥ ተመልከቱ።

በሶስት ሰዎች ቃል ቃሌን አፀናለሁ፣ ፤ ኔፊ ፲፤፩፣ ፫። ምስክሮች ለሰዎች ልጆች የእርሱን ቃል ምስክርነት ይሰጣሉ፣ ፤ ኔፊ ፳፯፣ ፲፤–፲፫። በሦስት ሰዎች አንደበት፣ እነዚህ ነገሮች ይፀናሉ፣ ኤተር ፭፣ ፬።

በእምነት ሶስቱ ምስክቶች ሰሌዳዎችን ያያሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፯።

የሙሴ ህግ። *ደግሞም ህግ፣ ሙሴ፣ ንጹህ እና ርኩስ፣ አሮናዊ ክህነት ተመልከቱ*

እግዚአብሔር ያላከበሩትን ታላቁን ህግ ለመተ ካት ለእስራኤል ቤት ህግጋትን በሙሴ በኩል ሰጠ (ዘፀአ. ፴፬፣ ፤ ዘፀአ. ፴፬፣ ፭–፪፣ ፤ ዘፀ.ት.፣ ዘዳግ. ፣ ፤ [ተጨማሪ])። የሙሴ ህግ ሰዎችን ስለ ሀላፊነቶቻቸው እንዲያስታውሱ የሚያደርጉ ብዙ መሰረታዊ መርሆችን፣ ደንቦችን፣ ቅደም ተከተ ሎችን፣ እና ምልክቶችን የያዙ ናቸው። ይህም እነ ርሱን ስለእግዚአብሔርና ለእርሱ ስላላቸው ሀላ ፊነት እንዲያስታውሱ የሚያደርግ (ሞዛያ ፣ ፣) ስነምግባራዊ፣ ግብረገባዊ፣ ሀይማኖታዊ ህግን እና ስጋዊ ትእዛዛትንና እንደ መስዋዕት (ዘሌዋ. ፩–፯) አይነት ድርጊቶችን የያዘ ነው። አስሩ ትእዛዛት እና ብዙ ሌሎቹ የግብረገባዊና የስነምግባር ዋጋ ትእዛዛት እንደነበሩ፣ እምነት ንስሀ መግባት፣ በውሀ መጠ መቅ፣ እና የኃጢያት ስርየት የህጉ ክፍሎች ናቸው። ብዙዎቹ የስርዓት ህጎች ደምን በማፍሰስ መስዋዕት ማድረግን በፈጸመው (አልማ ፴፬፣ ፲፫–፲፴) በኢየሱስ ሞት እና ትንሳኤ ተሟልተዋል። ህጉ የተፈጸመው በአሮናዊ ክህነት ስር ነበር እና ይህን የሚከተሉትን ወደክርስቶስ የሚያመጣ መዘጋጃ ወንጌል ነበር።

እንደ መጀመሪያውም ህግን እሰጣቸዋለሁ፣ ነገር ግን ይህም የስጋዊ ትእዛዝ ህግ ይሆናል፣ ጆ.ስ.ት.፣ ዘፀአ. ፴፬፣ ፩–፪።

ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚታችን ሆኖ አል፣ ገላ. ፣ ፤ ፲፱–፳፬።

የሙሴን ህግ እንጠብቃለን፣ እናም ህጉ እስከሚ ፈፀም ድረስ በፅኑነት ወደፊት ወደ ክርስቶስ እንመ ለከታለን፣ ፤ ኔፊ ፳፭፣ ፳፬–፴። ደህንነት በሙሴ ህግ ብቻ አይመጣም፣ ሞዛያ ፣ ፣ ፲–፲፣ ፴፪። በእኔም የሙሴ ህግ ተፈፀሟል፣ ፣ ኔፊ ፱፣ ፲፯። ለሙሴ የተ ሰጠው ህግ በእኔ መጨረሻ አለው፣ ፣ ኔፊ ፲፭፣ ፩–፣ ።

ባለመታዘዝ ምክንያት የሥጋ ትእዛዝ ሕግጋትን በመተው ሙሴን እና ቅዱስ ክህነትን ከእስራኤል ልጆች መካከላቸው አወጣ፣ ት. እና ቃ. ፳፬፣ ፳፫–፳፯።

የሙት ባህር

ከዮርዳኖስ ሸለቆ በደቡብ አካባቢ የሚገኝ የጨው ባህር። የጨው ባህርም ተብሎ ይታወቃል። የዚህ ውጪም ከሜድትሬኒያን ባህር ፫፻፶፭ ሜትር በታች ነው። ሰዶም፣ ገሞራ፣ እና ዞዓር ወይም ቤላ ከተማ ዎች በዚህ ዳርቻ አጠገብ ነበሩ (ዘፍጥ. ፲፱፣ ፭–፣)።

ትንቢትን በማሟላት እና እንደ አዳኝ ዳግም ምፅ ዓት ምልክቶች አንዱ፣ የሙት ባህር ውሀዎች ይፈ ወሳሉ፣ እናም በእዚያም ህይወት ይበለፅጋሉ (ሕዝ. ፴፯፣ ፰–፱)።

የሚስዮን ስራ። *ደግሞም መስበክ፣ ወንጌል ተመልከቱ*

የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልን በስራና በምሳሌ መካፈል።

መድኃኒትንም የሚያወራ እግሩ በተራሮች ላይ እጅግ ያማረ ነው፣ ኢሳ. ፶፪፣ ፯። እኔ ራሴ በጎቼን እሻለሁ እፈልግማለሁ፣ ሕዝ. ፴፬፣ ፲፩።

ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ፣ ማር. ፲፣ ፲፭ (ሞር. ፱፣ ፳፪)። አዝመራውም አሁን እንደ ነጣ እር ሻውን ተመልከቱ፣ ዮሐ. ፬፣ ፴፭። ካልተሳኩ እን ዴት ይሰብካሉ፣ ሮሜ ፣ ፣ ፲፭።

የእግዚአብሔርን ቃል በትጋት አስተምሯቸው፣ ያዕቆ. ፩፣ ፣ ፲፱። ጌታ ለሀገሮች ሁሉ ቃሉን እንዲያ ስተምሩ ሰጥቷል፣ አልማ ፳፱፣ ፳።

የወንጌሌ ሙላት በደካሞች እና በተራ ሰዎች ይታወጅ፣ ት. እና ቃ. ፩፣ ፳፫። በሰዎች ልጆች መካ ከል ድንቅ ስራ ሊመጣ ነው፣ ት. እና ቃ. ፤ ፩። በቀ ኖቻችሁ ሁሉ ብታገለግሉ፣ እናም አንድም ነፍስም ቢሆን እንኳን ወደ እኔ ብታመጡ፣ ደስታችሁ እን ዴት ታላቅ ይሆናል፣ ት. እና ቃ. ፲፰፣ ፲፭። በእኔ የተመረጡት ድምጼን ይሰማሉ እና ልባቸውን አያ ደንድኑም፣ ት. እና ቃ. ፳፤፣ ፯። ወንጌሌን በመስ በክ ሁለት በሁለት በመሆን ወደፊት ትሄዳላችሁ፣ ት. እና ቃ. ፴፪፣ ፯። ድምፅ ከዚህ ቦታ ሁሉ ወደፊት መሄድ አለበት፣ ት. እና ቃ. ፶፰፣ ፳፬። አፎቻችሁን ከፍታችሁ ወንጌሌን ስበኩ፣ ት. እና ቃ. ፫፭፣ ፩። በሰጠኋችሁ ራዕዮች እና ትእዛዛት በኩል እውነቶ ችን አውጁ፣ ት. እና ቃ. ፫፭፣ ፬። የተጠነቀቀ ሰው ጎረቤቱን ማስጠንቀቁ አስፈላጊ ነው፣ ት. እና ቃ. ፴፰፣ ፴፪ (ት. እና ቃ. ፴፰፣ ፴–፴፩)። ጌታ ወንጌ ልን ለሚሰብኩት ለቤተሰቦቻቸው እርዳታ ይሰጣል፣ ት. እና ቃ. ፲፤፣ ፣ ። የእግዚአብሔር አገልጋዮች ይሄዳሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፴፣ ፣ ፴፣ ። ታማኝ ሽማግ ሌዎችም ከዚህ ህይወት ሲሄዱ አገልግሎታቸውን ይቀጥላሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፴፣ ፣ ፲፯።

የሚስጥር ስብሰባ። *ደግሞም ቃየን፣ የጋድያንቶን ዘራፊዎች ተመልከቱ*

የቡድንን ክፉ አላማዎችን ለማከናወን በመሀላ አብረው የተሳሰሩ የሰዎች ድርጅት።

የሀሰት አባት የሰው ልጆችን በግድያ የሚስጥር

ሰብሰባ በጠበጠ፣ ፪ ኔፊ ፱፡፱። የጭለማ የሚስጥር ስራዎችን አጠፋ ዘንድ ያስፈልገኛል፣ ፪ ኔፊ ፲፡፲፭። የእግዚአብሔር ፍርድ በሚስጥራዊው ህብረት ላይ እንደዚህ መጣ፣ **አልማ** ፴፯፡፴። ጋድያንቶ የኔ ፊን ህዝብ መቡሉ ጥፋት ሊያመጣ ነበር፣ ሔሊ. ፪፡፱–፲፫። ሰይጣን በህዝቡ ልብ ውስጥ የሚስጥር መሀላ እና ቃል ኪዳን እንዲሰሩ አደረጋቸው፣ ሔሊ. ፯፡፳፭–፴፩። ጌታም በሚስጢራዊ ህብረት አይሰራም፣ **ኤተር** ፰፡፲፱። ሚስጢራዊ ህብረት የሚደግፍ ማንኛውም ሀገር ይጠፋል፣ **ኤተር** ፰፡፳፪–፳፫። እነርሱም በሚስጢራዊው ህብረት ምክንያት የነቢያቱን ቃላት በሙሉ አልተቀበሉም፣ **ኤተር** ፲፭፡፳፪።

ከቃየን ቀናት ጀምሮ፣ ሚስጥር ህብረቶች ነበሩ፣ ሙሴ ፭፡፶፭።

የሚያሰክር መጠጥ። የጥበብ ቃል *ተመልከቱ*

የማስተዋል ስጦታ። የመለየት ስጦታ *ተመልከቱ*

የማዕዘን ድንጋይ። *ደግምም* ኢየሱስ ክርስቶስ *ተመልከቱ*

የህንጻን መሰረት ማዕዘን የሚሰራበት ዋናው ድንጋይ። ኢየሱስ ክርስቶስ ዋና የማዕዘን ድንጋይ ተብሎ ተጠርቷል (ኤፌ. ፪፡፳)።

ግንበኞች የናቁት ድንጋይ፥ እርሱ የማዕዘን ራስ ሆነ፣ መዝ. ፻፲፰፡፳፪ (ማቴ. ፳፩፡፴፪–፴፭፡ ማር. ፲፪፡፲፡ ሉቃ. ፳፡፲፯፡ የሐዋ. ፬፡፲–፲፪)።

አይሁዶች የማዕዘን ድንጋይን አስወገዱ፣ *ያዕቆ.* ፪፡፲፭–፲፯።

የማይሞት፣ አለሟችነት። *ደግምም* ስጋዊ፣ የሚሞት፣ ትንሳኤ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ፣ ደህንነት *ተመልከቱ*

ለዘለአለም ከሞት በተነሳ ሁኔታ፣ ለስጋዊ ሞት ተገዝር በማይሆንበት የመኖር ጉዳይ።

ተነሥቶአል፣ ማር. ፲፮፡፮። እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉ፣ ፩ ቆሮ. ፲፭፡፳፪። የሚሞተው የማይሞተውን ሲለብስ፣ ሞት ድል በመነሣት ተዋጠ፣ ፩ ቆሮ. ፲፭፡፶፫–፶፭። ክርስቶስ ሞትን ሽሮአልና አለመጥፋትን አውጥቶአል፣ ፪ ጢሞ. ፩፡፲።

አለሟችነት ስጋና መንፈስ እንደነበሩ በድጋሚ ማገጣጠም ነው፣ ፪ ኔፊ ፱፡፲፫። መንፈሶች ከሰው ነታቸው ጋር አንድ በመሆን የማይጠፉ የማይሞቱ ይሆናሉ፣ **አልማ** ፲፩፡፴፭።

ታማኝ በዘላለም ሕይወት ዘውድ አክሊልም ይጫንላቸኋል፣ ት. እና ቃ. ፳፭፡፭። ምድር የተቀደሰች፣ የማትጠፋ ትሆናለች፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፩ (ት. እና ቃ. ፲፴፡፱)።

የሰውን ህያውነት እና ዘለአለማዊ ህይወት አምጥቶም የማሳለፍ የእግዚአብሔር ስራ እና ክብር ይህ ነው፣ ሙሴ ፩፡፴፱።

የማይጠፋ፣ የማይጠፋ ህይወት። የማይሞት፣ አለሟችነት *ተመልከቱ*

የምድር ዳርቻ። አለም—የአለም መጨረሻ *ተመልከቱ*

የሞት ቅጣት። *ደግሞም ግድያ ተመልከቱ*

ለተሰራ ወንጀል፣ በልዩም ከግድያ ቅጣት ጋር የተያያዘ፣ የሞት ቅጣት።

የሰውን ደም የሚያፈስስ ሁሉ ደሙ በሰው ይፈስሳል፣ ዘፍጥ. ፱፡፮ (ጆ.ስ.ት.፣ ዘፍጥ. ፱፡፲፪–፲፫)። ነፍሰ ገዳዩም ፈጽሞ ይገደል፣ ዘኁል. ፴፭፡፲፯።

እያወቀ የሚገድል ይሞታልና፣ ፪ ኔፊ ፱፡፴፭። በህግ መሰረት እንድትሞት ተፈርዶብሀል፣ **አልማ** ፩፡፲፫–፲፱። የገደለውም በሞት ተቀጥቷል፣ **አልማ** ፩፡፲፮። ህጉ የገደለውን ሰው ህይወት ይጠይቃል፣ **አልማ** ፴፱፡፲፪።

የሚገድልም ይገደላል፣ ት. እና ቃ. ፴፪፡፲፱።

የሞዛያ ልጆች። *ደግምም ሒምኒ፣ ሞዛያ፣ የቢንያም ልጅ፣ አሞን፣ የሞዛያ ወንድ ልጅ፣ አሮን፣ የሞዛያ ልጅ፣ ኦምነር ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ መልአክን ያዩ እና ንስሀ እንዲገቡ የጠራቸው የንጉስ ሞዛያ አራት ልጆች። ስማቸው አሞን፣ አሮን፣ ኦምነር፣ እና ሒምኒ ነበሩ (ሞዛያ ፳፯፡፴፱)። ለአስራ አራት አመት ወንጌልን ለላማናውያን በውጤታማነት በመስበክ አሳለፉ። በላማናውያን መካከል የነበረው አገልግሎታቸው መዝገብ የተሰጠው በመፅሐፈ አልማ፣ ምዕራፍ ፲፯ እስከ ፳፮ ውስጥ ነው።

በመጀመሪያ ቤተክርስቲያኗን ለማጥፋት የሞከሩ እምነት የሌላቸው ነበሩ፥ ሞዛያ ፳፯፡፲–፳፡ (አልማ ፴፯፡፮)። በመላዕክ ተገሰጸ እናም ንስሀ ገቡ፣ ሞዛያ ፳፯፡፲፩–፲፱፣ ፲፳–፳፡ ለላማናውያን ለመስበክ ፈቃድ አገኙ፣ ሞዛያ ፳፰፡፩–፮።

የሰለስቲያል ክብር። *ደግምም ከፍተኛነት፣ የክብር ደረጃዎች፣ የዘለዓለም ህይወት ተመልከቱ*

ሰው ከእዚህ ህይወት በኋላ ለማግኘት የሚችለው ከሶስቱ ከፍተኛው የክብር ደረጃ። በእዚህም ጻድቅ የሆነው ከእግዚአብሔር አብ እና ከልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ፊት ይኖራል።

ደግሞ ሰማያዊ አካል አንድ ነው፣ ፩ ቆሮ. ፲፭፡፴ (ት. እና ቃ. ፳፯፡፲፮)። ጳውሎስ ወደ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ ተነጠቀ፣ ፪ ቆሮ. ፲፪፡፪።

የሰለስቲያል ክብር በራዕይ ታየ፣ ት. እና ቃ. ፷፯፡–፷። ቅዱሳን በሰለስቲያል አለም ቦታ ከፈ ለጉ፣ መዘጋጀት አለባቸው፣ ት. እና ቃ. ፷፰፡፲። በሰለስቲያል መንግስት ህግጋት ለመኖር የማይ ችል በሰለስቲያል ክብር ለመኖር አይችልም፣ ት. እና ቃ. ፹፰፡፲፭–፳፪። በሰለስቲያል ክብር ውስጥ ሶስት ሰማያት አሉ፣ ከፍተኛውን የማግኘት ቅድመ ሁኔታ ተዘርዝረዋል፣ ት. እና ቃ. ፪፴፭፡፩–፪። በተጠያቂነት እድሜዎች ከመድረሳቸው በፊት የሞቱትን ልጆች ሁሉ በሰማይ ሰለስቲያል መንግ ስት ውስጥ ይድናሉ፣ ት. እና ቃ. ፪፴፯፡፲።

የሰማይ ሽንጎ። *ደግምም ቅድመ ምድራዊ ህይወት፤ የሰማይ ጦርነት፤ የቤዛነት ዕቅድ ተመልከቱ*

በቅድመ ምድራዊ ህይወት ወደዚህች ምድር ለሚመጡት ለመንፈስ ልጆቹ አብ አላማውን ያቀ ረበበት ጊዜ።

የእግዚአብሔርም ልጆች ሁሉ እልል አሉ፣ ኢዮብ ፴፰፡፩–፯። ዙፋኑንም ከእግዚአብሔር ከዋ ክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ፣ ኢሳ. ፲፬፡፲፪–፲፫።

በሰማይ ሰልፍ ሆነ፣ ራዕ. ፲፪፡፯–፲፩።

ከመወላዳቸው በፊት፣ የመጀመሪያውን ትም ህርት በመንፈሶች አለም ተቀበሉ፣ ት. እና ቃ. ፲፴፭፡፶፮።

ሰይጣን በቅድመ ምድራዊ ህይወት አመጸ፣ ሙሴ ፬፡፩–፬። አለም ከመፈጠሯ በፊት እውቀ ተኛዎችም ተደራጅተው ነበር፣ አብር. ፫፡፳፪። አምላኮች ተመካከሩ፣ አብር. ፬፡፳፯። አምላኮች የተማከሩባቸውን ስራዎች ጨረሱ፣ አብር. ፭፡፪።

የሰማይ አባት። *ደግምም እግዚአብሔር፣ አምላክ ተመልከቱ*

የሰው ዘር በሙሉ መንፈሶች አባት (መዝ. ፹፪፡፮፣ ማቴ. ፭፡፵፭፣ ዮሐ. ፣፡ ፴፬፣ ሮሜ ፰፡፲፮–፲፯፣ ገላ. ፬፡፯፣ ፭ ዮሐ. ፫፡፪)። ኢየሱስ የእርሱ በስጋ የተወለደ አንድያ ልጅ ነው። ሰው ለአብ ታዛዥ እንዲሆን እና እንዲያመልከው እንዲሁም በኢየሱስ ስም እንዲጸልይ ታዟል።

ለሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ብትሉ፥ የሰማዩ አባታችሁ እናንተን ደግሞ ይቅር ይላችኋልና፣ ማቴ. ፮፡፲፬ (ማቴ. ፲፰፡፴፭፣ ፣ ፤ ፤ ፲፫፡፲፬)። ይህ ሁሉ እንዲያስፈልጋችሁ የሰማዩ አባታችሁ ያውቃልና፣ ማቴ. ፮፡፳፮–፴፫ (ፍ ፤ ፤ ፲፫፡፳፮–፴፫)። በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው ነበር፣ ሉቃ. ፲፩፡፲፩–፲፫። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላ ክና አባት ይባረክ፣ ኤፌ. ፩፡፣። ለእዚህም እናንተም ለሰማይ አባታችሁ እዳ አለ ባችሁ፣ ሞዛያ ፪፡፴፬። ክርስቶስ የአብን ስም አክ ብሯል፣ ኤተር ፲፪፡፰። ቅዱሳን አብ ከተሰወረበት ቦታ ሲመጣ ስደታቸ ውን ምስክር ይስጡ፣ ት. እና ቃ. ፲፳፣፡፩–፣፡ ፯።

ከሰማይ አባታችን ታላቅ እና ግርማዊ በረከቶች አጋጠሙን፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡ ፳፣፡።

የሰማይ ጦርነት። *ደግምም ቅድመ ምድራዊ ህይወት፤ የሰማይ ሽንጎ ተመልከቱ*

በቅድመ ምድራዊ ህይወት ጊዜ በእግዚአብሔር የመንፈስ ልጆች መካከል የነበረ ጦርነት።

ሰይጣን ከሰማይ ወደ ምድር ተጣለ፣ ራዕ. ፲፪፡፩፣ ፯–፱።

ሰማን እና የሰማይ አንድ ሶስተኛዎች ተወረወሩ፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፴፯–፴፯። ሉሰፈር በአንድያ ልጅ ላይ አመጸ፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፳፭–፳፮።

ሰይጣን የአብን ክብር እና የሰው ነጻ ምርጫን ለማጥፋት ፈለገ፣ ሙሴ ፬፡፩–፬ (ኢሳ. ፲፬፡፲፪–፲፭፣ አብር. ፣፡ ፳፯–፳፰)። የመጀመሪያውን ሁኔ ታቸውን የጠበቁትም፣ ወደ ምድር መጡ፣ እናም ሰውነታቸውን ተቀበሉ፣ አብር. ፣፡ ፳፯።

የሰራዊት ጌታ። *ደግምም ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልከቱ*

የኢየሱስ ክርስቶስ ሌላ ስም። በሰማይና በምድር ሰራዊት ላይ ይነግሳል እናም ጻድቃንን በክፉዎች ላይ ይመራል (ት. እና ቃ. ፳፱፡፱፣ ፱፣ ፲፳፭፡፳፣)።

የጭፍሮች አምላክ እግዚአብሔር፥ እርሱ የክ ብር ንጉሥ ነው፣ መዝ. ፳፬፡፣፡ ፣ ።

የሰራዊት ጌታ የእስራኤል አምላክ ነው፣ ፮ ኔፊ ፳፡፪።

መንፈሴም ከሰው ጋር ሁል ግዜ አይሆንምና፣ ይላል የሰራዊት ጌታ፣ ት. እና ቃ. ፩፡ ፴፣፡።

የሰናፍጭ ቅንጣት

የሰናፍጭ አትክልት ቅንጣቱ በጣም ትንሽ ነው፣ ይህ የሚያድግበት የአትክልቱ ቁመት በጣም ትልቅ ነው። ኢየሱስ የሰማይ መንግስትን ከሰናፍጭ ቅን ጣት ጋር አነጻጸረ (ማቴ. ፣፣፡ ፴፩)።

የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል እምነት ቢኖራ ችሁ፥ ተራራን ለማንቀሳቀስ ትችላላችሁ፣ ማቴ. ፲፯፡፳።

የሰንበት ቀን። *ደግምም መፍጠር፣ ፍጥረት፤ እረፍት ተመልከቱ*

ለእረፍት እና ለማምለክ የተመደበ ቅዱስ ቀን እግዚአብሔር ሁሉንም ነገሮች ከፈጠረ በኋላ፣ በሰ ባተኛው ቀን አረፈ እናም ሰዎች እርሱን እንዲያስ ታውሱ በሳምንት አንድ ቀን የእረፍት ቀን እንዲ ሆን አዘዘ (ዘፀአ. ፳፡፰–፲፩)።

የሰው ልጅ

ከክርስቶስ ትንሳኤ በፊት፣ የቤተክርስቲያኗ አባላት፣ አይሁዶች እንደሚያደርጉት፣ የሳምንቱን መጨረሻ ቀን እንደ ሰንበት ያከብሩ ነበር። ከት ንሳኤ በኋላ፣ የቤተክርስቲያኗ አባላት፣ አይሁድም ይሁኑ አህዛብ፣ ስለጌታ ትንሳኤ ለማስታወስ የሳም ንቱን የመጀመሪያ ቀን (የጌታን ቀን) ያከብራሉ። ዛሬም ቤተክርስቲያኗ በሳምንት አንድ ቀንን እንደ ቅዱስ የሰንበት ቀን ታከብራለች፣ በዚህም ቀን እግ ዚአብሔርን ታመልካለች እንዲሁም ከአለም ስራ ዎች ታርፋለች።

የሰንበት ቀን ሰዎችን በመንፈስ ስለመመገብ እና በእግዚአብሔር ታዛዥ ለመሆን ስላላቸው ሀላፊነት እንዲያስታውሱ ያደርጋል። ህዝቦች ሰንበትን በማ ክበር ግዴለሽ በሚሆኑበት ጊዜ፣ የህይወት ሁሉም ሁኔታዎች ይነካሉ እናም የሀይማኖት ህይወታቸ ውም ይበሰብሳል (ነህ. ፲፫፡፲፭–፲፰፣ ኤር. ፲፯፡፳፩–፳፯)።

እግዚአብሔርም በሰባተኛውም ቀን ከሠራው ሥራ ሁሉ ዐረፈ፣ **ዘፍጥ.** ፪፡፩–፫። የእስራኤል ልጆች በሰንበት በና አልሰበሰቡም፣ **ዘፀአ.** ፲፮፡፳፪–፴። የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ፣ **ዘፀአ.** ፳፡፰–፲፩ (ሞዛያ ፲፫፡፲፯–፲፱)። ሰንበት በእግዚአ ብሔር በሰው መካከል ምልክት እንዲሆን ተሰጥቶ ነበር፣ **ዘፀአ.** ፴፩፡፲፪–፲፯ (ሕዝ. ፳፡፲፪፣ ፳)። በሰ ንበት ቀን አንግዛም አንሸጥም፣ ነህ. ፲፡፴፩። ሰንበ ትንም ደስታ፡ እግዚአብሔርም የቀደሰውን ክቡር ብትለው፡ የገዛ ፈቃድህንም ከማግኘት ተከልከል፣ **ኢሳ.** ፶፰፡፲፫–፲፬።

ሰንበት ስለ ሰው ተፈጥሮአል እንጂ ሰው ስለ ሰን በት አልተፈጠረም፣ **ማር.** ፪፡፳፫–፳፰። የሰው ልጅ የሰንበት ጌታ ነው፣ **ሉቃ.** ፮፡፩–፲። ኢየሱስ በም ኩራብ አስተማረ እናም በሰንበት ፈወሰ፣ **ሉቃ.** ፲፫፡፲–፲፬።

ኔፋውያን የሰንበትን ቀን ቅዱስ አድርገው ጠበቁ፣ **ጆረም** ፩፡፩። የሰንበትን ቀን አክብሩ፣ እናም ቀድ ሱት፣ **ሞዛያ** ፲፰፡፳፫።

በቅዱስ ቀኔም ቅዱስ ስነስርዓቶችህን አቅርብ፣ **ት. እና ቃ.** ፶፪፡፱–፲፫። የፅዮን ነዋሪዎች የሰንበት ቀንን ያክብሩ፣ **ት. እና ቃ.** ፳፳፡፳፱።

እኔ እግዚአብሔር ከምሰራው ስራ ሁሉ በሰባተ ኛው ቀን አረፍኩኝ፣ **ሙሴ** ፫፡፩–፫ (ዘፍጥ. ፪፡፩–፫፣ አብር. ፮፡፩–፫)።

የሰው ልጅ። *ደግምም ኢየሱስ ክርስቶስ፣ እግዚአብሔር፣ አምላክ ተመልከቱ*

ኢየሱስ ክርስቶስ ስለእራሱ በተናገረበት ጊዜ የተጠቀመበት ርዕስ (ሉቃ. ፱፡፳፪፣ ሉቃ. ፳፩፡፴፯)። ይህም የቅድስና ሰው ልጅ ማለት ነው። የቅድስና ሰው ከእግዚአብሔር አብ ስሞች አንዱ ነው። ኢየሱስ እራሱን እንደ ሰው ልጅ ሲጠራ፣ ይህም ከአብ ጋር ያለውን መለኮታዊ ግንኙነት በግ ልፅ ማወጁ ነበር። ይህ ርዕስ በብዙ ጊዜ በወንጌሎች ውስጥ ይገኛል። የኋለኛው ቀን ራዕይ የዚህ የአ ዳኝ ስምን ልዩ ትርጉም እና ቅዱስነትን አረጋገጠ (ት. እና ቃ. ፸፭፡፴፱፣ ፸፱፡፮፣ ፳፭፣ ፻፲፡፻፭፣ ሙሴ ፮፡፶፯)።

የሲና ተራራ። *ደግምም ሙሴ፣ የሙሴ ህግ ተመልከቱ*

ሙሴ እና እስራኤላውያን ከግብፅ ከተሰደዱ በኋላ ሶስት ወር የሰፈሩበት በውሀ በተከበበው በሲና ምድር ላይ ያለ ተራራ፣ ደግሞም የኮሬብ ተራራ ተብሎ ይጠራል (ዘፀአ. ፫፡፩)። በእዚህም እግዚአ ብሔር ለእስራኤል ቤት ህግን ለሙሴ ሰጨ፣ ደግ ሞም በእዚህ ድንኳኑ ተገንብቶ ነበር (ዘፀአ. ፲፱፡፪፣ ፳፡፲፰፣ ፳፬፡፲፪፣ ፴፪፡፲፪፣ ፴፬፡፲፫)።

የስነ ምግባር ጉድለት። *ስሜታዊ፣ ስሜታዊነት፣ በወሲብ የስነ ምግባር ጉድለት፣ ንጹህነት፣ ክፉ፣ ክፋት ተመልከቱ*

የራስ ማድረግ። *ደግምም አብርሐም— የአብርሐም ዘር፣ እስራኤል፣ የእግዚአብሔር ወንድ እና ሴት ልጆች፣ የክርስቶስ ልጆች ተመልከቱ*

ቅዱስ መጻህፍት ስለሁለት አይነት ራስ ማድረጊ ያዎች ይናገራሉ።

(፩) የእስራኤል ዝርያ ያልሆነ ሰው በኢየሱስ ክር ስቶስ እምነት፣ ንስሀ በመግባት፣ በማጥለቅ በመጠ መቅ፣ እና መንፈስ ቅዱስን በመቀበል የአብርሐም ቤተሰብ እና የእስራኤል ቤት አባል ለመሆን ይች ላል (፪ ኔፊ ፴፭፡፲፯–፲፰፣ ት. እና ቃ. ፴፬፡፫–፴፱፣ አብር. ፪፡፮፣ ፲–፲፩)።

(፪) የወንጌልን አዳኝ ስነስርዓት የተቀበሉ ሁሉ የእርሱን ትእዛዛት ለማክበር በመቀጠል የኢየሱስ ክርስቶስ ወንድ እና ሴት ልጆች ይሆናሉ (ሮሜ ፰፡፲፭–፲፯፣ ገላ. ፫፡፳፱–፳፱፣ ፬፡፭–፯፣ ሞዛያ ፭፡፯–፰)።

የርኩሰት ቤተክርስቲያን። *ዲያብሎስ— የዲያብሎስ ቤተክርስቲያን ተመልከቱ*

የርግብ መልእክት። *ደግሞም መንፈስ ቅዱስ ተመልከቱ*

መጥምቁ ዮሐንስ መሲህን ለማወቅ የሚችልበት ቀድሞ የተዘጋጀ ምልክት (ዮሐ. ፩፡፴፪–፴፬)። ጆሴፍ ስሚዝ የርግብ መልእክት እንደ መንፈስ ቅዱስ ምስክር ምድር ከመፈጠሯ በፊት የተጀመረ እንደሆነ አስተማረ፣ ስለዚህ፣ ዲያብሎስ በርግብ ምልክት ለመምጣት አይችልም።

መንፈስ እንደ ርግብ ወረደ፣ **ማቴ.** ፫፡፲፮።

ኢየሱስ ከተጠመቀም በኋላ፣ መንፈስ ቅዱስ ከሰማይ በእርግብ አምሳል ወረደ፣ ፤ ኔፊ ፲፩፡፳፯።

እኔ ዮሐንስ እመሰክራለሁ እና አስተውሉ፣ ሰማያት ተከፈቱ መንፈስ ቅዱስ እንደ ርግብ በእርሱ ላይ ወረደ፣ ት. እና ቃ. ፣ ፣ ።

የሮሜ ግዛት። *ደግምም ሮሜ ተመልከቱ*

የጥንት ሮሜ ግዛት። በሐዋሪያት ዘመን፣ የሮሜ ግዛት በአለም ውስጥ ታላቅ ሀይል ከነበራቸው አንዷ ነበረች። እርሷም በኤፍራጥስ፣ በዳንዩብ፣ በራይን፣ በአትላንቲክ፣ እና በሰሀራ በረሀ መካከል ያሉትን ሁሉ የያዘች ነበረች። ፖምፒየስ ኢየሩሳሌምን ሲይዝ፣ በ ምዓ. ፍልስጥኤም ድጋፍ የምትከተል ሀገር ሆነች። ምንም እንኳን ሮሜ አይሁዶችን ብዙ መብቶች ቢሰጧቸውም፣ አይሁዶች የሮሜ ግዛትን ጠሉ እናም በየጊዜውም ያምጹ ነበር።

የሮሜ ዜጋ የነበረው ጳውሎስ፣ በግዛቱ በልምድ የሚጠቀሙበት ቋንቋ የነበረውን የግሪክ ቋንቋ ወንጌልን በግዛት በሙሉ ለማሰራጨት ተጠቀመ።

የቋሚርን ለቁሚር አስረክቡ፣ ማቴ. ፣ ፡ ።

ጳውሎስ እንደ ሮሜ ዜጋ መብቱን ለመነ፣ የሐዋ. ፣ ፡ ።

የከሞራ ኮረብታ። *ደግምም መፅሐፈ ሞርሞን፣ ሞሮኒ፣ የሞርሞን ልጅ፣ ስሚዝ፣ ጆሴፍ ዳግማዊ ተመልከቱ*

በዩናይትድ ስቴትስ አሜሪካ፣ በምእራብ ኒውዮርክ ውስጥ የሚገኝ ትንሽ ኮረብታ። በዚህም ሞሮኒ የሚባል የጥንት ነቢይ አንዳንዱን የኔፋውያን እና የያሬዳውያን መዝገቦችን የያዘውን የወርቅ ሰሌዳዎች የደበቀበት ነው። በ (እ.አ.አ.) ጆሴፍ ስሚዝ እነዚህን ሰሌዳዎች እንዲያገኝና ከእነዚህ ክፍሎችም እንድተረጉም ወደዚህ ኮረብታ ከሞት በተነሳው ሞሮኒ ተመራ። ይህም ትርጉም መፅሐፈ ሞርሞን ነው።

ኔፋውያን በከሞራ ተሰበሰቡ፣ ሞር. ፣ ፡ ።

ከሞራ ብዙ ውሀ ያለበት ምድር ነበር፣ ሞር. ፣ ፡ ።

ሞርሞን መዝገቦችን በከሞራ ኮረብታ ደበቃቸው፣ ሞር. ፣ ፡ ። በከሞራ ኮረብታ ከሀያ አራት በቀር ሁሉም ተገድለው ነበር፣ ሞር. ፣ ፡ ።

ከከሞራ የምስራች ሰማን፣ ት. እና ቃ. ፣ ፡ ።

ጆሴፍ ስሚዝ ሰሌዳዎችን ከከሞራ ኮረብታ ወሰደ፣ ጆ.ስ.—ታ. ፣ ፡ ፣ ፡ ፣ ፡ ።

የቁጣ ስሜት። *ቁጣ ተመልከቱ*

የቃል ኪዳን ምድር

ጌታ ለታማኝ ተከታዮቹ፣ እናም በብዙ ጊዜ ለትውልዶቻቸው፣ እንደ ውርስ ቃል የሚገባላቸው ምድር። ብዙ የቃል ኪዳን ምድሮች አሉ። በብዙ ጊዜ በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ የሚናገሩበት የቃል ኪዳን ምድር በአሜሪካዎች ውስጥ ነው።

ይህችን ምድር ለዘርህ እሰጣለሁ፣ ዘፍጥ. ፣ ፡ (አብር. ፡ ፣ ፡ ።

የከነዓን ምድር ለአንተና ከአንተ በኋላ ለዘርህ እሰጣለሁ፣ ዘፍጥ. ፣ ፡ (ዘፍጥ. ፣ ፡ ።

ሙሴ በከነዓን ውስጥ የእስራኤል ምድር ዳርቻን ወሰነ፣ ዘኁል. ፣ ፡ (ዘኁል. ፣ ፡ ።

ወደ ቃል ኪዳንም ምድር ትመራለህ፣ ፤ ኔፊ ፡ ፣ ፡ (፤ ኔፊ ፡ ፣ ፡ ።

ጌታ ፃድቃንን በጣም አስፈላጊ ወደሆነው ምድር መራ፣ ፤ ኔፊ ፣ ፡ ።

የሌሂ ትውልዶች የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ካከበሩ፣ በቃል ኪዳን ምድር ውስጥ ይበለፅጋሉ፣ ፤ ኔፊ ፡ ፣ ፡ ።

እስራኤል ወደ ቃል ኪዳን ምድር ትመለሳለች፣ ፤ ኔፊ ፡ ፣ ፡ (ኢሳ. ፣ ፡ ።

ማንም ይህችን ምድር የራሱ ያደረገ ሀገር እግዚአብሔርን ያገለግላል፣ አለበለዚያ ይወገዳሉ፣ **ኤተር** ፡ ፣ ፡ ።

ስለዚህ፣ ይህም የቃል ኪዳን ምድር፣ እና ለፅዮን ከተማ ቦታም ነው፣ ት. እና ቃ. ፣ ፡ ።

ይሁዳ ወደ አብርሐም ምድር ለመመለስ ይጀምሩ፣ ት. እና ቃ. ፣ ፡ ።

አዲስታ ኢየሩሳሌም በአሜሪካ ክፍለ አህጉር ትመሰረታለች፣ እ.አ. ፣ ፡ ።

የቅድስና ሰው። *ደግምም እግዚአብሔር፣ አምላክ፣ የሰማይ አባት፣ የሰው ልጅ ተመልከቱ*

የአብ እግዚአብሔር ሌላ ስም (ሙሴ ፣ ፡ ።

የቢታንያ ማርያምን። *ደግሞም ማርታ፣ አልዓዛር ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ የአልዓዛርና የማርታ እህት።

ማርያም ቃሉን ልትሰማ በኢየሱስ እግር አጠገብ ተቀምጣ ነበረች፣ ሉቃ. ፣ ፡ ።

ማር ያም እና እህቷ ማርታ ኢየሱስን ጠሩ፣ ዮሐ. ፣ ፡ ።

የኢየሱስን እግር በሽቱ ንጥር ቀባች፣ ዮሐ. ፣ ፡ ።

የቤተመቅደስ ጋብቻ። ጋብቻ፣ መጋባት *ተመልከቱ*

የቤተሰብ ታሪክ። ለሙታን ደህንነት፣ የትውልድ ሐረግ *ተመልከቱ*

የቤተክርስቲያን መሪዎችን መደገፍ። *ደግሞም የጋራ ስምምነት ተመልከቱ*

በአጠቃላይ ለሚያገለግሉት እና ለቤተክርስቲያን መሪዎች እርዳታ ለመስጠት ቃል መግባት።

ኢያሱን በማኅበሩ ሁሉ ፊት አቁመው፥ እነርሱም

የቤተክርስቲያን ስም

እያዩ እዘዘው፣ ዘኍል. ፳፯፡፲፰–፲፱። ሕዝቡም ሁሉ ንጉሥ ሕያው ይሁን እያሉ እልልታ አደረጉ፣ ፩ ሳሙ. ፲፡፳፬። በነቢያቱም እመኑ፡ ነገሩም ይሰ ላላችኋል፣ ፪ ዜና ፳፡፳።

ለዋኖቻችሁ ታዘዙና ተገዙ፣ ዕብ. ፲፫፡፲፯።

አንተ ስላላጉረመረምክ በጌታ የተደገፍክ ትሆና ለህ፣ ፩ ኔፊ ፲፡፯። የዳኑትም ነቢያትን የተቀበሉት ናቸው፣ ፲ ኔፊ ፲፡፲፪–፲፫። እነዚህ አስራ ሁለትን አድምጡ፣ ፲ ኔፊ ፲፪፡፩።

በእኔ ድምጽ ሆነ በአገልጋዮቼ ድምጽ፣ ያም አንድ ነው፣ ት. እና ቃ. ፩፡፴፰። ቃሉን ልክ ከእኔ አፍ እንደወጣ አድርጋችሁ ትቀበላላችሁ፣ ት. እና ቃ. ፳፩፡፭። አገልጋዮቼን የሚቀበል፣ እኔን ይቀበላል፣ ት. እና ቃ. ፴፡፭፡ ፴፯–፴፰። እኔን የሚቀበል፣ የላኳ ቸውን ይቀበላል፣ ት. እና ቃ. ፲፣፲፪፡፳። ህዝቦቼ እነ ዚህን የመደብኳቸውን ድምፅ ካላዳመጡ፣ አይባረ ኩም፣ ት. እና ቃ. ፲፳፬፡፶–፶፮።

የቤተክርስቲያን ስም። *ደግምም ሞርሞን* (ሞርሞኖች)፤ *የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን*፤ *የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ ከትንሳኤው ከአ ጭር ጊዜ በኋላ ኢየሱስ ጻድቅ ኔፋውያንን በጎበኘ በት ጊዜ፣ ቤተክርስቲያኑ ስሙን የያዘ ይሁን አለ (፫ ኔፊ ፳፯፡፫–፰)። በዚህም ዘመን ጌታ የቤተክ ርስቲያኑን ስም “የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን” እንድትባል ገልጿል (ት. እና ቃ. ፲፣፲፭፡፱)።

የቤዛነት ዕቅድ። *ደግምም ኢየሱስ ክርስቶስ*፤ *ወንጌል*፤ *የኃጢያት ዋጋን መክፈል*፤ *የኃጢያት ክፍያ*፤ *የአዳም እና የሔዋን ውድቀት*፤ *ደህንነት ተመልከቱ*

የሰው አለሟችነትን እና ዘለአለማዊ ህይወ ትን ለማምጣት የተነደፈ የኢየሱስ ክርስቶስ ወን ጌል ሙላት። ይህም እግዚአብሔር ከሰጣቸው ህግጋት፣ ስርዓቶች፣ እና ትምህርቶች ጋር ፍጥረ ትን፣ ውድቀትን፣ እና የኃጢያት ክፍያን በተጨ ማሪ የያዘ ነው። ይህ እቅድ ሁሉም ሰዎች ከፍ ከፍ እንዲሉና ከእግዚአብሔር ጋር ለዘለአለም ለመ ኖር እንዲችሉ ያደርጋል (፪ ኔፊ ፪፣ ፱)። በቅዱ ሳት መጻህፍት ደግሞም ይህ አላማ እንደ ደህን ነት አላማ፣ የደስታ አላማ፣ እና የምህረት አላማ ተብሎ ይጠራል።

እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፣ ኢሳ. ፶፫፡፭ (ሞዛያ ፲፭፡፭)።

ለመዳን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለም፣ የሐዋ. ፬፡፲፪። ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉ፣ ፩ ቆሮ. ፲፭፡፳፪። ጻጋው በእምነት አድኖአችኋል፣ ኤፌ. ፪፡፰ (፪ ኔፊ ፳፭፡፳፫)። የእግዚአብሔር በዘ ላለምም ሕይወት ተሰፋ ከዘላለም ዘመናት በፊት ተሰፋ ሰጠ፣ ቲቶ ፩፡፪። ኢየሱስ የዘለአለም ደህ ንነት ጸሀፊ ነው፣ ዕብ. ፭፡፰–፱። የደህንነት አላማ ለሙታንም ተሰጥቷል፣ ፩ ጴጥ. ፫፡፲፰–፳፣ ፬፡፮ (ት. እና ቃ. ፲፣፴፰)።

ሞት የታላቁ ፈጣሪ የምህረት አላማን ያሟላል፣ ፪ ኔፊ ፱፡፮። የአምላካችን ዕቅድ እንዴት ታላቅ ነው፣ ፪ ኔፊ ፱፡፲፫። የቤዛነት ዕቅድ ከሞት መነ ሳትን እና የኃጢያቶች ስርየትን ያመጣል፣ **አልማ** ፲፪፡፳፭–፴፪። አሮን ለላሞኒ አባት ስለቤዛነት ዕቅድ አስተማረ፣ **አልማ** ፳፪፡፲፪–፲፬። አሙሌቅ የቤዛነት ዕቅድን ገለጸ፣ **አልማ** ፴፬፡፲–፲፮። አልማ የቤዛነት ዕቅድን ገለጸ፣ **አልማ** ፴፪፡፭–፳፯፣ ፴፬፡፭።

የፍጥረት፣ የውድቀት፣ የኃጢያት ክፍያ፣ እና የጥምቀት ትምህርቶች በእዚህ ዘመን ራዕይ ተረጋ ግጥጠዋል፣ ት. እና ቃ. ፳፡፲፣–፳፱። ዕቅዱ ከአ ለም ፍጥረት በፊት ተመድቦ ነበር፣ ት. እና ቃ. ፲፳፯፡፳፪።

የሰውን ህያውነት እና ዘለአለማዊ ህይወት አምጥ ቶም የማሳለፍ ስራዬ እና ክብሬ ይህም ነው፣ ሙሴ ፩፡፴፱። ይህ የሰው ሁሉ የደህንነት እቅድ ነው፣ ሙሴ ፮፡፶፪–፶፪። በዚህ እንፈትናቸዋለን፣ አብር. ፫፡፳፪–፳፯።

የተመረጠ (ቅጽል ወይም ስም)። *ደግምም ጥሪ*፤ *በእግዚአብሔር መጠራት*፤ *የተጠራበት ተመልከቱ*

ለልዩ ሀላፊነቶች በእግዚአብሔር የተመረጥ።

ከመረጥሁት ጋር ቃል ኪዳኔን አደረግሁ፣ መዝ. ፹፱፡፫።

ቅዱሳን የተመረጠ ትውልድ፣ የንጉሥ ካህናት ናቸው፣ ፩ ጴጥ. ፪፡፱።

ክርስቶስ ከመጀመሪያ ጀምሮ የእግዚአብሔር ውድና ተወዳጁ ነበር፣ ሙሴ ፬፡፪።

የተሰበረ ልብ። *ደግምም ልብ*፤ *መስዋዕት*፤ *መጸጸት*፤ *ንስሀ መግባት*፤ *ትሁት*፤ *ትሕትና*፤ *ገር*፣ *ገርነት ተመልከቱ*

የተሰበረ ልብ መኖር ትሁት፣ የተጸጸተ፣ ንስሀ የገባ፣ እና የዋህ መሆን ማለት ነው—ያም ለእግዚ አብሔር ፈቃድ ተቀባይ መሆን ነው።

የተቀጠቀጠና የተዋረደ መንፈስ ካለው ጋር እኖ ራለሁ፣ ኢሳ. ፶፯፡፲፭።

ክርስቶስ የተሰበረ ልብና የተዋረደ መንፈስ ላላ ቸው እራሱን አቀረበ፣ ፪ ኔፊ ፪፡፯። ለጌታ እንደ መስዋዕት የተሰበረ ልብ እና የተዋረደ መንፈስ አቅ ርቡ፣ ፫ ኔፊ ፱፡፳ (ት. እና ቃ. ፶፱፡፳)። ልባቸው የተሰበረና መንፈሳቸው የተዋረደ ብቻ ናቸው ወደ ጥምቀት የተቀበሉት፣ ሞሮኒ ፮፡፪።

ኢየሱስ የተሰቀለው ልባቸው ለተዋረደው ኃጢያት ስርየት ነው፣ ት. እና ቃ. ፷፭፡፱። መንፈሱ የተዋረደው ተቀባይ ነው፣ ት. እና ቃ. ፶፪፡፲፮። ለተዋረዱት መንፈስ ቅዱስ ቃል ተገብቷል፣ ት. እና ቃ. ፶፭፡፲። መንፈሴ ትሁቱን እና የተዋረደውን ለማብራራት ተልኳል፣ ት. እና ቃ. ፲፱፯፡፱፣ ፲፱።

የተራራ ስብከት። *ደግምም ኢየሱስ ክርስቶስ፤ እርካታ ተመልከቱ*

በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሚስዮን ሊላኩ ለነበሩት ለደቀ መዛሙርቱ የተሰጠ ንግግር (ማቴ. ፭–፯፣ ሉቃ. ፮፡፳–፴፱)። ጌታ ስብከቱን አስራ ሁለቱን ከጠራ ከትንሽ ጊዜ በኋላ ሰጠ።

ስብከቱ በጆሴፍ ስሚዝ የመፅሐፍ ቅዱስ ትርጉም ውስጥ እና የስብከቱ አስፈላጊ ክፍሎች በማቴዎስ ከሚገኘው መዝገብ ውስጥ እንደጠፉ በሚያሳየው በቮ ኔፊ ፲፪–፲፬ ውስጥ በመተመዘገበው አንድ አይነት ስብከት በተጨማሪ ግልፅ ሆኗል።

የተቀባው። *ደግምም መሲህ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልከቱ*

ኢየሱስ *ክርስቶስ* (የግሪክ ቃል) ወይም *መሲሕ* (የአራሜይክ ቃል) ተብሎ ተጠርቷል። ሁለቱም ቃላቶች “የተቀባው” ማለት ናቸው። የሰው ዘርን ደህንነት በሚመለከት በሁሉም ነገሮች የአብ ወኪል እንዲሆን በአብ *የተቀባው* እርሱ ነው።

እግዚአብሔር ቀብቶኛልና፣ ኢሳ. ፷፩፡፩–፫።

ወንጌልን ይሰብክ ዘንድ ቀብቶታል፣ ሉቃ. ፬፡፲፯–፳፪። ኢየሱስ በ እግዚአብሔር አብ ተቀብቷል፣ የሐዋ. ፬፡፳፯። እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስ ቀባው፣ የሐዋ. ፲፡፴፰።

የተቀየሩ ሰዎች

ጉዳትን ወይም ሞትን ወደ ዘለአለማዊነት በት ንሳኤ እስከሚነሱ ድረስ እንዳይቀምሱ የተለወጡ ሰዎች።

ሄኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ አልተገኘም፤ እግዚአብሔር ወስዶታልና፣ ዘፍጥ. ፭፡፳፬ (ዕብ. ፲፩፡፭፣ ት. እና ቃ. ፻፲፡፶–፶፱)። እስከ ዛሬም ድረስ የሙሴን መቃብር ማንም አላ ወቀም፣ ዘዳግ. ፴፬፡፭–፮ (አልማ ፶፭፡፲፱)። ኤል ያስም በዐውሎ ነፋስ ወደ ሰማይ ወጣ፣ ፪ ነገሥ. ፪፡፲፩።

እስከመጣ ድረስ ይኖር ዘንድ ብወድስ ምን አግዶህ፣ ዮሐ. ፳፩፡፳፪–፳፫ (ት. እና ቃ. ፮፡፩–፫)።

ሞትን በጭራሽ አትቀምሱም፣ ፫ ኔፊ ፳፰፡፮። ሞትን እንዳይቀምሱ፣ በሰውነታቸው ላይ ለውጥ ተደርጓል፣ ፫ ኔፊ ፳፰፡፴፰ (፬ ኔፊ ፩፡፲፬፣ ሞር. ፰፡፲–፲፩)።

ተወዳጁ ዮሐንስ ጌታ እስከሚመጣ ድረስ ይኖራል፣ ት. እና ቃ. ፮። የሄኖክን ፅዮን ወደ እቅፈ የወሰድኩት እኔው ነኝ፣ ት. እና ቃ. ፴፯፡፬ (ሙሴ ፮፡፳፩፣ ፴፩፣ ፴፱)። ሔኖክ እና ወንድሞቹ እስከ ጽድቅ ቀን ድረስ የምቆጥባት ከተማ ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፵፭፡፲፩–፲፪። ኤልያስ ሞትን ሳይቀምስ ወደሰማይ ተወሰደ፣ ት. እና ቃ. ፲፣ ፲፫።

መንፈስ ቅዱስ በብዙዎች ላይ አረፈ፣ እና እነርሱም በሰማይ ሀይሎች ወደ ፅዮን አረጉ፣ ሙሴ ፮፡፳፯።

የተከለከለ ፍሬ። *ዔድን፤ የአዳም እና የሔዋን ውድቀት ተመልከቱ*

የተዋረደ መንፈስ። *የተሰበረ ልብ ተመልከቱ*

የተጠያቂነት እድሜ። *ልጅ፣ ልጆች፤ መልስ መስጠት፣ ሂሳብ፣ ተጠያቂነት፣ ሀላፊነት፤ የህጻን ጥምቀት፤ ጥምቀት፣ መጥመቅ—ጥምቀት ለህጻናት አይደለም ተመልከቱ*

የታላቅ ዋጋ ዕንቁ። *ደግምም ስሚዝ፣ ጆሴፍ ዳግማዊ፤ ቀኖና፤ ቅዱሳት መጻህፍት ተመልከቱ*

በምድር ላይ ያለው የእግዚአብሔር መንግስት “ታላቅ ዋጋ ካለው ዕንቁ” ጋር ተመሳስሏል (ማቴ. ፲፫፡፴፭–፴፮)።

የታላቅ ዋጋ ዕንቁ ይፋ ከሆኑት ከኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አራት ቅዱሣት መጻህፍት መካከል ለአንዱ የተሰጠ ስም ነው። የታላቅ ዋጋ ዕንቁ በመጀመሪያ የታተመው በ፲፰፻፹፭ (እ.አ.አ.) ነበር እናም አሁን በትምህርት እና ቃል ኪዳኖች ውስጥ የሚገኙት አንዳንድ ነገሮችን ያለው ነበር። ከ፲፱፻፹ (እ.አ.አ.) ጀምሮ የታተሙት እትሞች (፩) ከጆሴፍ ስሚዝ የኦሪት ዘፍጥረት ትርጉም የተወሰዱ መፅሐፈ ሙሴ የሚባሉትን ክፍሎች፣ እና ጆሴፍ ስሚዝ—ማቴዎስ ተብሎ የሚጠራ የማቴዎስ ፳፬፡፣ (፪) በ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.) ጆሴፍ ስሚዝ ከግብጻዊ ፓፓይረስ የተተረጎመ መፅሐፈ አብርሐም ተብሎ የሚታወቅ መፅሐፍን፤ (፫) በ፲፰፻፴፯ (እ.አ.አ.) የጆሴፍ ስሚዝ—ታሪክ ተብለው የሚታወቁ ከጆሴፍ ስሚዝ የቤተክርስቲያኗ ታሪክ የተወሰዱ ታሪኮችን፣ እና (፬) አስራ ሶስት የእምነት እና የትምህርት መረጃዎች የሆንይትን የእምነት አንቀጾችን የያዘ ነው።

የትብብር ስርዓት። *ደግምም መቀደስ፣ የቅድስና ህግ ተመልከቱ*

በዳግም በተመለሰችው ቤተክርስቲያን በመጀመሪያው ቀናት ቅዱሳን የቅድስናን ህግ በመከተል ለመኖር የጣሩበት ድርጅት። ግላሰቦች ንብረቶችን፣ እቃዎችን፣ እና ትርፍን በፍላጎታቸው

እና በሚያስፈልጋቸው መሰረት በመቀበል እነዚህን ነገሮች ይካፈላሉ ነበር። (ት. እና ቃ. ፶፩፥፫፤ ፸፰፥፩–፲፭፤ ፻፬)።

በስጋዊ ነገሮች እኩል ሁኑ፣ ት. እና ቃ. ፸፥፲፬። ቅዱሳን በሁሉም ነገሮች እኩል እንዲሆኑ ይደራጁ፣ ት. እና ቃ. ፸፰፥፫–፲፩ (ት. እና ቃ. ፹፪፥፲፯–፳)። ጌታ ለትብብር ስርዓት ራዕይ እና ትእዛዝ ሰጠ፣ ት. እና ቃ. ፺፪፥፩። ጆን ጆንሰን የትብብር ስርዓት አባል ይሁን፣ ት. እና ቃ. ፺፯፥፯–፱። ጌታ የትብብር ስርዓትን የማስተዳደሪያ አጠቃላይ መመሪያ ሰጠ፣ ት. እና ቃ. ፻፬። ህዝቦቼ በሰለስቲያል መንግስት ህግ በኩል አስፈላጊ በሆነው ህብረት መሰረት አይተባበሩም፣ ት. እና ቃ. ፻፭፥፩–፲፫።

የትውልድ ሐረግ። *ደግሞም ለሙታን ደህንነት፤ ስነስርዓቶች—የወኪል ስነስርዓት፤ ቤተሰብ፤ የመታሰቢያ መፅሐፍ፤ ደህንነት፤ ጥምቀት፣ መጥመቅ—ለሙታን መጠመቅ ተመልከቱ*

በቤተሰብ ውስጥ ትውልዶችን የሚከታተል መዝገብ። የክህነት ባለስልጣንነት ወይም የተለያዩ በረከቶች ለልዩ ቤተሰብ የተለዩ በሆኑበት፣ የቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ የትውልድ ሐረግ በጣም አስፈላጊ ነው (ዘፍጥ. ፭፤ ፲፤ ፳፭፤ ፴፮፤ ፩ ዜና ፩–፱፤ ዕዝ. ፪፥፷፩–፷፪፤ ነሀ. ፯፥፷፫–፷፬፤ ማቴ. ፩፥፩–፲፯፤ ሉቃ. ፫፥፳፫–፴፰፤ ፩ ኔፊ ፫፥፩–፬፤ ፭፥፲፬–፲፱፤ ጄረም ፩፥፩–፪)። ዛሬ ዳግም በተመለሰችው ቤተክርስቲያን ውስጥ፣ የቤተክርስቲያን አባላት በግማሽ ሙታን ትውልዳቸውን በማወቅ የሚያድኑ ስርዓቶችን ትውልዳቸውን በመወከል ለማከናወን የቤተሰብ ትውልዳቸውን ይፈልጋሉ። እነዚህ ስነስርዓቶች ተቀባይ የሚሆኑት በመንፈስ አለም ውስጥ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልን ለተቀበሉት ሙታኖች ነው (ት. እና ቃ. ፻፳፯–፻፳፰)።

የኃጢያት ስርየት። *ደግሞም መጸጸት፣ ንስሀ መግባት፤ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ፤ ይቅርታ ማድረግ ተመልከቱ*

በንስሀ መግባት ላይ በመመካት ይቅርታ ማድረግ። የኃጢያት ስርየት ሊሆን የተቻለው በኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢያት ክፍያ በኩል ነው። ሰው የኃጢያት ስርየትን የሚቀበለው በክርስቶስ እምነት ላለው፣ ለኃጢያቶቹ ከተጠመቀ፣ የጥምቀት እና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ለመቀበል እጆች የመጫን ስነስራአቶችን ከተቀበለ፣ እና የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ካከበረ ነው። (እ.አ. ፩፥፫–፬)።

ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነጻለች፤ እንደ ደምም ብትቀላ እንደ ባዘቶ ትጠራለች፣ ኢሳ. ፩፥፲፰–፲፰።

ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ስርየት የሚፈስ ደሜ ይህ ነው፣ ማቴ. ፳፮፥፳፰ (ዕብ. ፱፥፳፪–፳፰፣ ት. እና ቃ. ፳፯፥፪)። ንስሐ ግቡ፥ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ ተጠመቁ፣ የሐዋ. ፪፥፴፰ (ሉቃ. ፫፥፫፣ ት. እና ቃ. ፻፯፥፳)። በኢየሱስ የሚያምን ሁሉ የኃጢአቱን ስርየት ይቀበላሉ፣ የሐዋ. ፲፥፵፫ (ሞዛያ ፫፥፲፫)።

ለኃጢአታቸው ስርየት መመልከት ያለባቸው ወደ ክርስቶስ ነው፣ ፪ ኔፊ ፳፭፥፳፮። የኃጢያቶችን ስርየት ለማግኘት፣ ደሀዎችን እና እርዳታ የሚፈልጉትን መንከባከብ ይገባናል፣ ሞዛያ ፬፥፲፩–፲፪፣ ፳፮። ማንኛውም ንስሃ የሚገቡ ለኃጢአታቸው ስርየት ይገባቸዋል፣ አልማ ፲፪፥፴፬። ትዕዛዙን መፈፀም የኃጢያት ስርየትን ያመጣል፣ ሞሮኒ ፰፥፳፭።

የአሮናዊ ክህነት ለኃጢያት ስርየት በማጥለቅ የመጥመቅ ቁልፎች የያዘ ነው፣ ት. እና ቃ. ፲፫ (ት. እና ቃ. ፹፬፥፳፬፣ ፸፬፣ እ.አ. ፩፥፬)። እኔ ጌታ ኃጢያቶቻቸውን ደግሜ አላስታውሳቸውም፣ ት. እና ቃ. ፶፰፥፵፪–፵፫ (ሕዝ. ፲፰፥፳፩–፳፪)። ለኃጢያት ስርየት የውክልና ጥምቀትን ተምረው ነበር፣ ት. እና ቃ. ፻፴፰፥፴፫።

የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ። *ደግሞም መሀሪ፣ ምህረት፤ መሰቀል፤ መስቀል፤ መስዋዕት፤ መጸጸት፣ ንስሀ መግባት፤ ማፅደቅ፣ ከበደል ነጻ መሆን፤ ቅዱስ ቁርባን፤ ቅድስና፤ ቤዛ፣ ማዳን፣ ቤዛነት፤ ትንሳኤ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ የኃጢያት ስርየት፤ የማይሞት፣ አለሟችነት፤ የቤዛነት ዕቅድ፤ የአዳም እና የሔዋን ውድቀት፤ የእግዚአብሔር ወንድ እና ሴት ልጆች፤ የክርስቶስ ልጆች፤ ይቅርታ ማድረግ፤ ደህንነት፤ ደም፤ ጌቴሴማኒ፤ ጸጋ ተመልከቱ*

ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር ማስታረቅ።

በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ እንደሚጠቀሙበት፣ የኀጢያት ዋጋን መክፈል ለኃጢያት ስራ ቅጣትን መቀበል፣ በዚህም ንስሀ ከሚገባው ኃጥያተኛ ላይ የኃጢያትን ውጤት ማስወገድ እና ከእግዚአብሔር ጋር እንዲታረቅ መፍቀድ ማለት ነው። ለሰው ዘር ሁሉ ፍጹም የሆነ የኀጢያት ክፍያ ለማድረግ የሚችለው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነበር። ይህን ለማድረግ የቻለው አለም ከመፈጠሯ በፊት በነበረው ታላቅ ሸንጎ በመመረጡ እና ቀድሞ በመሾሙ (ኤተር ፫፥፲፬፤ ሙሴ ፬፥፩–፪፤ አብር. ፫፥፳፯)፣ በመለኮታዊ ልጅነቱ፣ እና ኃጢያት በሌለው ህይወቱ ምክንያት ነው። የኀጢያት ክፍያው ለሰው ዘር ኀጥያቶች የተሰቃየበትን፣ የደሙ መፍሰስን፣ እና ሞቱን እና በተከተለው ከመቃብር በትንሳኤ መነሳቱን የሚጨምር ነው (ኢሳይያስ ፶፫፥፫–፲፪፤ ሉቃ. ፳፪፥፵፬፤ ሞዛያ ፫፥፭–፲፩፤ አልማ ፯፥፲–፲፫፤ ት. እና ቃ. ፲፱፥፲፮–፲፱)። በኃጢያት ክፍያ ምክ

ንያት፣ ሁሉም ሰዎች ከማይሞቱ ሰውነቶች ጋር ከሞት ይነሳሉ (፩ ቆሮ. ፲፭፡፳፪)። የኃጢያት ክፍያም ከጎጥያታችን ምህረት የምናገኝበት እና ከእግዚአብሔር ለዘለአለም የምንኖርበት መንገዶች ሰጥቶናል። የአቅመ አዳም እድሜ ላይ የደረሰ እና ህግን የተቀበለ ሰው እነዚህን በረከቶች ለመቀበል የሚችለው በኢየሱስ ክርስቶስ ካመነ፣ ለጎጥያቶቹ ንስሀ ከገባ፣ የደህናነትን ስርዓቶችን እና የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ከተቀበለ ብቻ ነው። የአቅመ አዳም እድሜ ያልደረሱት እና ህግ የሌላቸው በኃጢያት ክፍያ በኩል ቤዛነት ያገኛሉ (ሞዛያ ፲፭፡፳፫–፳፭፤ ሞሮኒ ፰፡፳፪)። ክርስቶስ ለጎጥያቶቻችን ክፍያ ካልሰጠ በስተቀር፣ ምንም ህግ፣ ስርዓት፣ ወይም መስዋዕት የፍትህን ጥያቄ ለመመለስ አይችልም፣ እና ሰው ወደ እግዚአብሔር ፊት ዳግሞ መመለስ አይችለም (፪ ኔፊ ፪፡ ፱) ብለው ቅዱስ መጻሕፍት በግልጽ አስተምረዋል።

ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው፣ ማቴ. ፳፮፡፳፰። ወዙም እንደ ደም ነጠብጣብ ነበረ፣ ሉቃ. ፳፪፡ ፴፱–፴፬። እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው፣ ዮሐ. ፮፡ ፶፩። ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፣ ዮሐ. ፲፩፡ ፳፭። ክርስቶስ ለሚታዘዙለት ሁሉ የዘላለም መዳን ምክንያት ነው፣ ዕብ. ፭፡ ፱። በክርስቶስ ደም መፍሰስ እኛም ተቀድሰናል፣ ዕብ. ፱፣ ፲፡ ፩–፲። ክርስቶስ አንድ ጊዜ በኃጢአቶች ምክንያት ተሰቃይቷል፣ ፩ ጴጥ. ፫፡ ፲፰። የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል፣ ፩ ዮሐ. ፩፡ ፯።

ለኃጢያቶች በመስቀል ላይ ተሰቀለና ተገደለ፣ ፩ ኔፊ ፲፩፡ ፴፪–፴፫። ደህንነት የሚመጣው የተሰበረ ልብ እናም የተዋረደ መንፈስ ላላቸው ነው፣ ፪ ኔፊ ፪፡ ፫–፲፣ ፳፭–፳፯። እራሱን ለኃጢያት መስዋዕት አቀረበ፣ ፪ ኔፊ ፪፡ ፯። የኃጢያት ክፍያው ለሰዎች ከውድቀት ቤዛ ሆናቸው እናም ከሞትና ከሲኦል አዳናቸው፣ ፪ ኔፊ ፱፡ ፭–፳፱። ወሰን የሌለው የኃጢያት ክፍያ ይኖር ዘንድ ያስፈልጋል፣ ፪ ኔፊ ፱፡ ፯። በክርስቶስ የኃጢያት ክፍያ ከእርሱ ታረቁ፣ ያዕቆ. ፬፡ ፲፩። ባለማወቅ ኃጢያትን ለፈፀሙት የእርሱ ደም የኃጥያቶች ክፍያ ይሆናል፣ ሞዛያ ፫፡ ፲፩–፲፭። ሰው በኃጢያት ክፍያ ደህንነትን ይቀበላል፣ ሞዛያ ፬፡ ፯–፰። ኃጢያት ክፍያን ባያደርገው ኖሮ መወገድ በማይችሉበት ሁኔታ መጥፋት ነበረባቸው፣ ሞዛያ ፲፫፡ ፳፯–፴፪። ለዓለም ኃጢያት ክፍያን ይከፍላል፣ አልማ ፴፬፡ ፰–፲፯። የምህረትን ዕቅድ ለመፈፀም እግዚአብሔር እራሱ ለዓለም ኃጥያቶች የኃጢያት ክፍያ ይሆናል፣ አልማ ፴፪፡ ፲፩–፴። የምድር ሁሉ አምላክ ነኝ፣ ለዓለም ኃጥያቶችም ተገድያለሁ፣ ፫ ኔፊ ፲፩፡ ፲፡

እኔ እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች ለሁሉም ሰዎች ተሰቃይቻለሁ፣ ት. እና ቃ. ፲፱፡ ፲፯። ህጻናት በአንድያ ልጄ ድነዋል፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡ ፴፯–፴፯። እኔ እግዚአብሔር ነገሮች ለሁሉም ሰዎች ተሰቃይቻለሁ፣ ት. እና ቃ. ፴፭፡ ፫–፭።

ይህ ነገር የአብ አንድያ ልጅ መስዋዕት አም ሳል ነው፣ ሙሴ ፭፡ ፯። የሰው ዘሮች ሁሉ በክርስቶስ ኃጢያት ክፍያ በኩል መዳን ይችላሉ፣ እ.አ. ፩፡ ፫።

የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን። *ደግሞም የቤተክርስቲያን ስም፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን፣ የእውነተኛ ቤተክርስቲያን ምልክቶች፣ የወንጌል ዳግም መመለስ ተመልከቱ*

የኋለኛው ቀናት የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን ከሌላው ዘመን ቤተክርስቲያናት ለመለየት የተሰጠ ስም፣ (ት. እና ቃ. ፲፱፡ ፫–፱)።

ጌታ እውቀቶችን በኋለኛው ቀን ቅዱሳን ላይ ያፈስሣል፣ ት. እና ቃ. ፲፳፩፡ ፴፫። ጆሴፍ ስሚዝ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ነቢይና ባለራዕይ ነው፣ ት. እና ቃ. ፲፳፯፡ ፲፪። የጌታ ታላቅ ቀን ለኋለኛው ቀን ቅዱሳን ደርሷል፣ ት. እና ቃ. ፲፳፯፡ ፳፩፣ ፳፱። ጆሴፍ ስሚዝ የኋለኛው ቀን ቅዱሳንን ለመሰብሰብ ረዳ፣ ት. እና ቃ. ፲፴፭፡ ፫። የኋለኛው ቀን ቅዱሳን ወደ ደቡብ ዩናይትድ ስቴትስ ክፍለ አገሮች ለመጓዝ በቡድን ተደራጁ፣ ት. እና ቃ. ፲፴፮፡ ፪። የጋብቻ ህግጋት ለኋለኛው ቀን ቅዱሳን ተገለጹ፣ ኦ.አ. ፩። ለኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ብቁ ለሆኑ ወንድ አባላት በሙሉ ክህነት ተሰጠ፣ ኦ.አ. ፪።

ለኋለኛው ቀን ቅዱሳን የተሰጠ የመጀመሪያው ራዕይ ታሪክ፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡ ፩።

የነህስ ሰሌዳዎች። *ደግሞም ሰሌዳዎች ተመልከቱ*

ከመጀመሪያ ጀምሮ እስከ ፯፻ ም.ዓ. ድረስ የብዙ ነቢያትን ፅሁፎች የያዘ በአይሁዶች የተጠበቀ መዝገብ (፩ ኔፊ ፭፡ ፣–፣፯)። ይህ መዝገብ በኢየሩሳሌም ውስጥ ከአይሁዶች ሽማግሌዎች መካከል አንዱ በሆነው በላባን ይጠበቅ ነበር። ሌሂ እና ቤተሰቡ በም ድረበዳ ውስጥ እያሉ፣ ሌሂ ወንድ ልጆቹን ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው ይህን መዝገብ እንዲያገኙ ላካቸው (፩ ኔፊ ፣–፱)። (ለተጨማሪ መረጃ፣ በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ የሚገኘውን “ስለመፅሐፈ ሞርሞን አጭር መግለጫ” ተመልከቱ።)

የነቢያት ትምህርት ቤት። *ደግሞም ስሚዝ፣ ጆሴፍ ዳግማዊ ተመልከቱ*

በከርትላንድ፣ ኦሀዮ (ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ) ውስጥ፣ በ፲፰፻፴፪–፻፴፯ (እ.አ.አ.)

ክረምት፣ ስለ ወንጌል እና ስለእግዚአብሔር መን ግስት በተመለከተ በሁሉንም ነገሮች ወንድሞችን ለማሰልጠን ጌታ ጆሴፍ ስሚዝን ትምህርት ቤት እንዲያደራጅ አዘዘው። ከዚህም ትምህርት ቤ ብዙዎቹ የቤተክርስቲያኗ መሪዎች መጥተዋል። ሌላ የነቢያት ወይም የሽማግሌዎች ትምህርት ቤት በጃክሰን የግዛት ክፍል፣ ምዙሪ ውስጥ በፓርሊ ፒ ፕራት ተመራ (ት. እና ቃ. ፶፯፡፩–፯)። እንደዚህ አይነት ትምህርት ቤቶች ቅዱሳን ቀደ ምዕራብ ከተ ሰደዱ በኋላ ተጀምረው ነበር፣ ነገር ግን እነዚህ ወዲ ያው እንዲቆሙ ተደረጉ። አሁን የወንጌል ትምህ ርት በቤት፣ በክህነት ስልታን ቡድኖች፣ እና በተ ለያዩ ደጋፊ ድርጅቶች፣ እንዲሁም በቤተክርስ ቲያኗ ትምህርት ቤቶች፣ መንፈሳዊ ኮሌጆችና፣ በሀይማኖት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ነው የሚከ ናወኑት።

ራሳችሁን ቀድሱ እናም የመንግስትን ትምህርት እርስ በራስ አስተምሩ፣ ት. እና ቃ. ፹፯፡፷–፹። በትጋት ፈልጉ እና እርስ በራስም አስተምሩ፣ ት. እና ቃ. ፹፯፡፲፲–፲፭፹፪። የነቢያት ትምህርት ቤት ስርዓት ተመድቧል፣ ት. እና ቃ. ፹፯፡፲፭፯–፲፱፭። ቀዳሚ አመራር የነቢያት ትምህርት ቤት ቁልፎችን ይዘዋል፣ ት. እና ቃ. ፶፡፯–፯።

የነፃነት አርማ። *ደግምም ሞሮኒ፣ ሻምበል ተመልከቱ*

በመፅሀፈ ሞርሞን ውስጥ፣ በኔፋውያን ወታደ ሮች ዋና መሪ ሞሮኒ የተነሳ አርማ። ሞሮኒ አርማውን የሰራም የኔፋውያን ህዝቦች ሀይማኖታቸውን፣ ነጻነ ታቸውን፣ ሰላማቸውን፣ እና ቤተሰቦቻቸውን ለመ ጠበቅ ለማነሳሳት ነበር።

ሞሮኒ ኮቱን ቀድዶ የነፃነት አርማ ሰራ፣ **አልማ** ፴፮፡፲፪–፲፮። አርማውን የሚደግፉ ቃል ኪዳን ገቡ፣ **አልማ** ፴፮፡፳–፳፪። ሞሮኒ በሰገነት ላይ የነ ፃነት ዓርማው እንዲሰቀል አደረገ፣ **አልማ** ፴፮፡፴፯ (አልማ ፴፩፡፳)።

የናስ እባብ። *ደግምም ሙሴ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልከቱ*

በእግዚአብሔር ትእዛዝ በመርዛማ እባቦች የተ ነከሱትን እስራኤላውያን ለማዳን ሙሴ የሰራው የናስ እባብ (ዘኁል. ፳፩፡፰–፱)። የናስ እባብ በእ ንጨት ላይ ተሰቀለ እናም "ቀና ብሎ የተመለከተ እንዲኖር ዘንድ ተሰቀለ" (አልማ ፴፫፡፲፱–፳፪)። ጌታ ስለእባቡ በምድረበዳ ውስጥ መሰቀል በመስ ቀል ላይ እራሱ እንደተሰቀለበት ምልክት ጠቅሶ ታል (ዮሐ. ፫፡፲፬–፲፭)። የኋለኛ ቀን ራዕይ የመ ርዛማው እባብ ታሪክን እና ሰዎች እንዴት እንደ ዳኑ ያረጋግጣል (፩ ኔፊ ፲፯፡፴፩፣ ፪ ኔፊ ፳፭፡፭፡፳፣ ሔለ. ፰፡፲፬–፲፭)።

የንጉሱ የሆኑት ሰዎች

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ የኔፋውያንን መንግ ስት ለመጣል የፈለጉ ቡድኖች (አልማ ፶፩፡፩–፰)።

የኖኅ ዘመን የጥፋት ውሀ። *ደግሞም መርከብ፣ ቀስተ ዳመና፣ ኖኅ፣ የመፅሐፍ ቅዱስ የአባቶች አለቃ ተመልከቱ*

በኖህ ዘመን ምድር በሙሉ በውሀ ሰምጣ ነበር። ይህም የምድር ጥምቀትና ጽዳት ምሳሌ ነበር (፩ ጴጥ. ፫፡፳–፳፩)።

እግዚአብሔር ሥጋን ሁሉ ለማጥፋት በም ድር ላይ የጥፋት ውኃን ያመጣል፣ ዘፍጥ. ፮፡፲፯ (ሙሴ ፯፡፴፭፣ ፴፫–፴፪፣ ፴፡፲፯፣ ፴፡፲፯፣ ፴)። ከሰ ባት ቀንም በኋላ የጥፋት ውኃ በምድር ላይ ሆነ፣ ዘፍጥ. ፯፡፲። እግዚአብሔር ቀስቱን በደመና ላይ እንደ ቃል ኪዳን ምልክት አስቀመጠ፣ ዘፍጥ. ፱፡፱–፲፯።

ውኃውም ከምድሪቱ ገፅ ከሸሸ በኋላ የአሜሪካ መሬት ከሁሉም መሬት በላይ የተመረጠች ምድር ሆነች፣ **ኤተር** ፲፫፡፪።

ክፉው በጥፋት ውሀ ይሞታል፣ **ሙሴ** ፯፡፴፯፣ ፴፡፳፬።

የአለም መጨረሻ፣ የአለም ዳርቻ፣ የምድር ዳርቻ። *አለም—የአለም መጨረሻ ተመልከቱ*

የአስራ ሁለቱ ሽንጎ። *ሐዋሪያ ተመልከቱ*

የአስራ ሁለቱ ቡድን። *ሐዋሪያ ተመልከቱ*

የአስቆሮቱ ይሁዳ

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከኢየሱስ አስራ ሁለት ሐዋሪያት አንዱ (ማቴ. ፲፡፬፣ ማር. ፣፲፡፣ ዮሐ. ፮፡፷፭፣ ፲፪፡፭)። የአባቱ ስም "የቂርዮት ሰው" ማለት ነው። እርሱም ከይሁዳ ጎሳ የመጣ ነበር እናም ከገሊላ የመጣ ብቸኛ ሐዋሪያ ነበር። ይሁዳ ጌታን አሳልፎ ሰጠ።

ኢየሱስን ለካህናት አለቆች አንዱ አሳልፎ በመ ስጠቱ ሰላሳ ብር ተቀበለ፣ **ማቴ.** ፳፮፡፲፬–፲፮ (ዘካ. ፲፩፡፲፪–፲፫)። ጌታን በመሳም አሳልፎ ሰጠ፣ **ማቴ.** ፳፮፡፴፯–፴ (ማር. ፲፬፡፴፫–፴፭፣ ሉቃ. ፳፪፡፴፯–፴፰፣ ዮሐ. ፲፰፡፪–፭)። እራሱን አንቆ ሞተ፣ **ማቴ.** ፳፯፡፭። ሰይጣንም በይሁዳ ገባ፣ **ሉቃ.** ፳፪፡፫ (ዮሐ. ፲፫፡፪፣ ፳፯፡፴–፴)። ዳዊት ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ መስጠቱን ተናገረ፣ **የሐዋ.** ፩፡፲፯ (መዝ. ፴፩፡፱)።

የአርማትያስ ዮሴፍ

የአርማትያስ ዮሴፍ የሳንሀድሪን አባል፣ የክር ስቶስ ደቀ መዛሙርት፣ እና በጌታ መኮነን ምንም ተሳታፊ ያለሆነ ሀብታም እና ታማኝ እስራኤላ

ውያን። ከስቅለት በኋላ፣ ዮሴፍ የኢየሱስን ሰውነት በንጹህ በተልባ እግር ልብስ ከፈነ እናም በዮሴፍ በተወቀረ መቃብር ውስጥ አሳረፈው፣ (ማቴ. ፳፯፡፶፱–፷፣ ማር. ፲፭፡፵፫–፵፮፣ ሉቃ. ፳፫፡፶–፶፫፣ ዮሐ. ፲፱፡፴፰–፴፪)።

የአባቶች አለቃ፣ ፓትሪያርክ። *ደግሞም ሚች አባት፣ ወንጌል ሰባኪ፣ የመልከ ጼዴቅ ክህነት፣ የፓትሪያርክ በረከቶች ተመልከቱ*

ቅዱሣት መጻህፍት ለዚህ ሁለት አይነት ትርጉም ይሰጣሉ፥ (፩) በመልከ ጼዴቅ ክህነት ውስጥ የተሾመ ሀላፊነት፣ አንዳንዴም ወንጌል ሰባኪ ተብለው ይጠራሉ፣ (፪) የቤተሰቦች አባቶች። የተሾሙ ፓትሪያርኮች ብቁ ለሆኑ የቤተክርስቲያን አባላት ልዩ በረከቶችን ይሰጣሉ።

የተሾሙ ፓትሪያርክ፣ ሌሎቹም ነቢያት፥ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች ሰጠ፣ **ኤፌ.** ፬፡፲፩ (እ.አ. ፩፡፲፯)።

ወንጌል ሰባኪዎችን መሾም የአስራሁለቱ ሀላፊነት ነው፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፴፱። ሀይረም ክህነት እና የፓትሪያርክ ሀላፊነትን ይውሰድ፣ ት. እና ቃ. ፲፳፬፡፶፩–፶፪፣ ፲፳፬፡፲፣ ፲፴፭፡፩።

አባቶች፣ ያዕቆብ ልጆቹን እና ትውልዶቻቸውን ባረከ፣ **ዘፍጥ.** ፴፱፡፩–፳፰።

ስለ አባቶች አለቃ ዳዊት በግልጥ ልናገር፣ **የሐዋ.** ፪፡፳፱።

ሌሂ ትውልዶቹን መከረ እናም ባረከ፣ ፪ ኔፊ ፩፡፲–፲፩።

መብት ያለው ወራሽ፣ የአባቶችን መብት የሚይዘው ሊቀ ካህን ሆንኩኝ፣ **አብር.** ፩፡፪–፬።

የአብርሐም ቃል ኪዳን። *ደግሞም መግረዝ፣ ቃል ኪዳን፣ አብርሐም ተመልከቱ*

አብርሐም ወንጌልን ተቀበለ እና ወደ ሊቀ ካህነት ተሾመ (ት. እና ቃ. ፹፬፡፲፣ አብር. ፪፡፲፩)፣ የዘለአለማዊነት ቃል ኪዳን ወደሆነው ወደ ሰለስቲያል ጋብቻ ገባ (ት. እና ቃ. ፲፴፭፡፩–፬፡፲ ፲፴፪፡፲፱፣ ፳፰)። አብርሐም የእነዚህ ቃል ኪዳናት በረከቶች ሁሉ ለስጋዊ ዝርያው እንደሚሰጥ የተሰፋ ቃል ተሰጠው (ት. እና ቃ. ፲፴፪፡፳፰፱–፴፩፣ አብር. ፪፡፯–፲፩)። እነዚህ ቃል ኪዳናት እና የተሰፋ ቃላት አብረው የአብርሐም ቃል ኪዳን ተብለው ይጠራሉ። የዚህ ቃል ኪዳን ዳግሞ መመለስ በመጨረሻው ቀናት ወንጌል ዳግሞ መመለስ ነው፣ በዚህም በኩል የምድር ህዝቦች ሁሉ ተባርከዋል (ገላ. ፫፡፯–፱፣ ፳፰፡፱፣ ት. እና ቃ. ፲፲፡፲፪፣ ፲፳፭፡፲፣ ፲፱፡፲–፲፭፣ አብር. ፪፡፲–፲፩)።

የአብርሐም ዘር። *አብርሐም—የአብርሐም ዘር ተመልከቱ*

የአዳም እና የሔዋን ውድቀት። *ደግሞም ሔዋን፣ መንፈሳዊ ሞት፣ ስጋዊ ሞት፣ ስጋዊ፣ የሚሞት፣ ቤዛ፣ ማዳን፣ ቤዛነት፣ አዳም፣ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ፣ የቤዛነት ዕቅድ፣ ፍጥረታዊ ሰው ተመልከቱ*

የሰው ዘር በእዚህች ምድር ላይ ሟች የሆነበት ሁኔታ። አዳም እና ሔዋን የተከለከለውን ፍሬ በበሉበት ጊዜ፣ ሟች፣ የኃጢያት እና ሞት ተገዢ ሆኑ። አዳም በምድረም ላይ "የመጀመሪያ ስጋ" ሆነ (ሙሴ ፫፡፯)። የኋለኛው ቀን ራዕይ ውድቀት በረከት እንደሆነ እናም አዳምና ሔዋን እንደ ሰው ዘር ሁሉ የመጀምሪያ ወላጆች መከበር እንዳለባቸው ግልፅ አደረገ።

ውድቀት በሰው እድገት አስፈላጊ የሆነ እርምጃ ነበር። እግዚአብሔር ውድቀት እንደሚመጣ ስላወቀ፣ በቅድመ ምድራዊ ህይወት ለአዳኝ እቅድ አድርጎ ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ ለአዳም ውድቀት ደግሞም በሰው ንስሀ መግባት በኩል ለሰው የግል ኃጢያቶች የኃጢያት ዋጋን ለመክፈል በመካከለኛው ዘመን መጣ።

ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና፣ **ዘፍጥ.** ፪፡፲፯ (ሙሴ ፫፡፲፣ ፲፯)። ከፍሬውም ወሰደችና በላች፣ **ዘፍጥ.** ፫፡፮ (ሙሴ ፬፡፲፪)።

ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና፣ ፩ ቆሮ. ፲፭፡፳፪።

የሰው ዘር በመሳትና በውድቀት ላይ ነበሩ፣ ፩ ኔፊ ፲፡፮። ከሰው ልጅ ውድቀት ጀምሮ መንገዱ ተዘጋጅቷል፣ ፪ ኔፊ ፪፡፬። አዳምና ሔዋን የተከለከለውን ፍሬ ከበሉ በኋላ፣ ከኤድን ገነት ወጡ፣ ፪ ኔፊ ፪፡፲፱። ሰዎች ይኖሩ ዘንድ አዳም ወደቀ፣ ፪ ኔፊ ፪፡፲፭–፳፮። ተፈጥሮአዊው ሰው ለእግዚአብሔር ጠላት ነበረ፣ ሞዛያ ፫፡፲፱። አሮን የላሞኒን አባት ስለውድቀት አስተማረ፣ **አልማ** ፳፪፡፲፪–፲፡። የኃጢያት ክፍያ መኖሩ አስፈላጊ ነውና አለበለዚያ የሰው ዘር ሁሉ መጥፋት እንዳለባቸው የማይቀር ነበር፣ **አልማ** ፴፡፡፱። የመጀመሪያ ወላጆቻችን ከጌታ ፊት ለጊዜውም ይሁን በመንፈስ ተለይተዋል፣ **አልማ** ፴፪፡፪–፲፭ (ሔለ. ፲፡፲–፲፯)። በውድቀትም የተነሳ ተፈጥሮአችን ክፉ ሆኗል፣ **ኤተር** ፫፡፪።

እነዚህን ቅዱስ ህጎችን በመተላለፍ ሰዎች ስጋዊና አጋንንታዊ ሆኑ፣ ት. እና ቃ. ፳፡፳ (ት. እና ቃ. ፳፱፡፴–፴፱)።

እንደወደክም ለመዳን ትችላለህ፣ **ሙሴ** ፩፡፱–፲፪። በመተላለፍ ምክንያት ውድቀት መጥቷል፣ **ሙሴ** ፮፡፶፱። ሰዎች በእራሳቸው ኃጥያቶች ይቀጣሉ፣ **እ.አ.** ፩፡፪።

የኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ እና ሞት ምልክቶች። *ደግምም ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልክቱ*

ከኢየሱስ ክርስቶስን መወለድ እና ሞት ጋር የሚገናኙ ድርጊቶች።

መወለድ፣ ድንግል ትፀንሳለች፥ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፣ ኢሳ. ፯፥፲፬። ከቤተ ልሔም በእስራኤልም ላይ ገዥ የሚሆን ይወጣልኛል፣ ሚክ. ፭፥፪።

ላማናውያኑ ሳሙኤል አንድ ቀን፣ ማታ፣ እና ቀን ብርሀን እንደሚኖር፤ አዲስ ኮከብ፣ እና ሌሎች ምልክቶች እንደሚታዩ ተነበ፣ ሔለ. ፲፬፥፪–፯። ምልክቶቹ ተሟለተዋል፣ ፫ ኔፊ ፩፥፲፭–፳፩።

ሞት፣ ላማናውያኑ ሳሙኤል ጭለማ፣ ነጎድጓዶችና መብረቆች፣ እና የምድር መንቀጥቀጥን ተነበየ፣ ሔለ. ፲፬፥፳–፳፯። ምልክቶቹ ተሟለተዋል፣ ፫ ኔፊ ፰፥፭–፳፫።

የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን። *ደግምም ቅዱሳን፣ የጎለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን፣ የቤተክርስቲያን ስም፣ የእውነተኛ ቤተክርስቲያን ምልክቶች፣ የእግዚአብሔር መንግስት ወይም መንግስተ ሰማያት፣ የወንጌል ዳግም መመለስ ተመልክቱ*

በጥምቀት እና በመረጋገጥ የኢየሱስ ክርስቶስን ስም በራሳቸው ላይ የወሰዱ የሚያምኑ ሰዎች ድርጅት። እውነተኛ ቤተክርስቲያን ለመሆን ይህም የጌታ ቤተክርስቲያን መሆን አለበት፣ የእርሱ ስልጣን፣ ትምህርቶች፣ ህግጋት፣ ስነስርዓቶች፣ እና ስም ሊኖረው ይገባዋል፤ እንዲሁም እርሱ በመደባቸው ወኪሎቹ በኩል እርሱ ይህን መግዛት አለበት።

ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በቤተክርስቲያኗ ላይ ጨምሯል፣ የሐዋ. ፪፥፵፯። ብዙዎች ስን ሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን፣ ሮሜ ፲፪፥፭። እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድ ንሆን ተጠምቀናል፣ ፩ ቆሮ. ፲፪፥፲፫። ቤክርስቲያኗ በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ተጸንሳለች፣ ኤፌ. ፪፥፲፱–፳። ሐዋሪያትና ነቢያት ለቤተክርስቲያኗ አስፈላጊ ናቸው፣ ኤፌ. ፬፡፲፩–፲፯። ክርስቶስ የቤተክርስቲያን ራስ ነው፣ ኤፌ. ፭፥፳፫።

ብዙ ቤተክርስቲያኖች ቢኖሩም ሁሉም አንድ ቤተክርስቲያን ነበሩ፣ ሞዛያ ፳፭፥፲፱–፳፪። ቤተክርስቲያኗ ጻዳች እናም በስርዓት ተስተካከለች፣ አልማ ፮፥፩–፯። የክርስቶስ ቤተክርስቲያን በስሙ መጠራት አለባት፣ ፫ ኔፊ ፳፯፥፰። ለመፆምና ለመፀለይ እንዲሁም ለመነጋገር ሁልጊዜ በቤተክርስቲያን ተገናኙ፣ ሞሮኒ ፮፥፭።

ይህች እውነተኛና ህያው ቤተክርስቲያን ናት፣ ት. እና ቃ. ፩፥፴። የክርስቶስ ቤተክርስቲያን በእነዚህ በመጨረሻው ቀናት ተነሳች፣ ት. እና ቃ. ፳፭፥፩። ጌታ ቤተክርስቲያኑን እንዲገነቡ አገልጋዮቹን ጠራ፣ ት. እና ቃ. ፴፱፥፲፫። እንደዚህም ቤተክርስቲያኗ በመጨረሻው ቀናት ትጠራለች፣ ት. እና ቃ. ፻፲፭፥፬።

የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት። *ደግምም ማጎግ፣ አርማጌዶን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ የጊዜዎች ምልክቶች፣ ጎግ ተመልክቱ*

በአንድ ዚህ አመት ዘመን መጀምሪያ ላይ፣ ክርስቶስ ወደ ምድር ይመለሳል። ይህም ድርጊት የምድርን ስጋዊ የሙከራ ጊዜ መጨረሻን ይጠቁማል። ኃጢያተኞች ከምድር ይወጣሉ እናም ምድር በምትጻዳበት ጊዜ ጻድቃን በዳመና ይነጠቃሉ። ክርስቶስ መቼ ለሁለተኛ ጊዜ እንደሚመጣ ማንም ሰው ባያውቅም፣ ጊዜው እየቀረበ እንደሆነ የምንመለከታቸው ምልክቶች ሰጥቶናል፣ (ማቴ. ፳፬፣ ጆ.ስ.—ማቴ. ፩)።

እኔን ግን የሚቤዝኝ ሕያው እንደ ሆነ፥ በመጨረሻም ዘመን በምድር ላይ እንዲቆም አውቃለሁ፣ ኢዮብ ፲፱፣ ፳፭። ጕልበት ሁሉ ለእኔ ይንበረከካል፥ ምላስም ሁሉ በእኔ ይምላል፣ ኢሳ. ፵፭፥፳፫ (ት. እና ቃ. ፹፯፥፲፪)። የሰው ልጅ ከሰማይ ደመናት ጋር መጣ፣ ዳን. ፯፥፲፫ (ማቴ. ፳፭፥፳፬፣ ሉቃ. ፳፩፥፳፭–፳፯)። ወደ እርሱም ወደ ወጉት ይመለከታሉ፣ ዘካ. ፲፪፥፲። ሰውም። ይህ በእጅህ መካከል ያለ ቍስል ምንድር ነው? ይለዋል፣ ዘካ. ፲፫፡፮ (ት. እና ቃ. ፵፭፥፶፩)። እርሱ እንደ አንጥረኛ እሳትና ነውና የሚመጣበትን ቀን መታገሥ የሚችል ማን ነው፣ ሚል. ፫፥፪ (፫ ኔፊ ፳፬፡፪፣ ት. እና ቃ. ፲፳፯፥፳፩)።

የሰው ልጅ በአባቱ ክብር ይመጣል፣ ማቴ. ፲፮፥፳፯ (ማቴ. ፳፭፥፴፩)። ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን ከአባት ብቻ በቀር የሚያውቅ የለም፣ ማቴ. ፳፬፡፴፮ (ት. እና ቃ. ፴፱፡፯፣ ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፥፴፯–፴፯)። ይህ ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት፥ እንዲሁ ይመጣል፣ የሐዋ. ፩፥፲፩። ጌታ ራሱ ከሰማይ ይወርዳልና፣ ፩ ተሰ. ፬፡፲፮። የጌታው ቀን ግን እንደ ሌባ ሆኖ ይመጣል፣ ፪ ጴጥ. ፫፡፲። ጌታ ከብዙ ሺህ ቅዱሳኑ ጋር ይመጣል፣ ይሁዳ ፩፥፲፬። ከደመና ጋር ይመጣል፤ ዓይንም ሁሉ ያዩታል፣ ራዕ. ፩፥፯።

ኢየሱስ አመምን ለመፍረድ ይቆማል፣ ፫ ኔፊ ፳፯፡፲፬–፲፰።

ተዘጋጁ ተዘጋጁ፤ ጌታ ተቃርቧልና፣ ት. እና ቃ. ፩፥፲፪። ራሴን ከሰማይ በኃይል እገልጣለሁ፣ በምድር ላይ ለአንድ ሺ አመታት እኖራለሁ፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፱–፲፪። ድምጻችሁን ከፍ አድርጉ እናም ንስሀ መግባትን ጩሁ፣ የጌታን መንገድ ለዳግም ምፅዓቱ አዘጋጁ፣ ት. እና ቃ. ፴፬፡፭–፲፪። እኔ ኢየሱስ ክርስቶስ ነኝ፤ እናም በድንገትም

ወደ ቤተመቅደሴ እመጣለሁ፣ ት. እና ቃ. ፴፯፡፳ (ት. እና ቃ. ፯፴፫፡፪)። የምታዩኝ ቀን በቶሎም ይምጣል፣ እናም እኔም እንደሆንኩ ታውቃላ ችሁ፣ ት. እና ቃ. ፴፰፡፳። እኔን የሚፈራም ስለ ጌታ መምጫ ታላቅ ቀን፣ እንዲሁም የሰው ልጅ መምጫ ምልክቶችን፣ ይጠብቃል፣ ት. እና ቃ. ፶፭፡፴፱። የጌታ ፊትም ይገለጻል፣ ት. እና ቃ. ፹፰፡፣፶፭። ታላቁና የሚያስፈራው የጌታ ቀን ቅርብ ነው፣ ት. እና ቃ. ፯፲፡፲፯። አዳኝ በሚመ ጣበት ጊዜ እርሱ እንዳለ እናየዋለን፣ ት. እና ቃ. ፯፴፡፩። አዳኝ፣ በህዝቦቹ መካከል ይቆማል፣ እና በሁሉም ስጋዎች መካከል ይነግሳል፣ ት. እና ቃ. ፯፴፫፡፳፭። ከእግዚአብሔር ከሰማይ ውስጥ የወረ ደው፣ ልብሱም የቀላ ከባሶራ የሚመጣ ማን ነው፣ ት. እና ቃ. ፯፴፫፡፶፯ (ኢሳ. ፷፫፡፩)።

የኢየሩሳሌም ሐናንያ

በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ እርሱ እና ባለቤቱ ሰጲራ ለጌታ የቀደሱትን ገንዘብ ድርሻን በማስቀረት ለጌታ ዋሹ። ጴጥሮስ ፊት ለፊት ሲጋፈጣቸው፣ ወደ ምድር ወደቁ እና ሞቱ (የሐዋ. ፭፡፩–፲፩)።

የኤጲስ ቆጶስ አመራር

በቤተክርስቲያኗ ውስጥ አጠቃላይ ባለስልጣን። በቤተክርስቲያኗ ምድራዊ ደህንነት ላይ አጠቃላይ ሀላፊነት አለው (ት. እና ቃ. ፲፯፡፳፯)። የአጠቃ ላይ ባለስልጣን የሆኑት የኤጲስ ቆጶስ አመራር እና አማካሪዎቹ በቤተክርስቲያኗ የአሮናዊ የክህነት ባለ ስልጣኖችን በሙሉ ይመራሉ (ት. እና ቃ. ፳፯፡፲፯–፲፯፣ ፲፯፡፫፣ ፲፯–፲፰)።

ኤድዋርድ ፓርትሪጅ ኤጲስ ቆጶስነት ይሾም፣ ት. እና ቃ. ፶፭፡፱። ኤጲስ ቆጶሳት በቀዳሚ አመ ራር ይጠሩ እና ይለዩ፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፲፩–፲፭። በኩራት የሆኑ፣ የአሮን ተወላጅ የሆኑት በቀዳሚ አመራር ለመሪነት ለመጠራት፣ መለየት፣ እና ለመ ሾም መብት አላቸው፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፲፣ ፲፯–፳። በቀዳሚ አመራር ፊት ብቻ ነው ለፍርድ የሚ ቀርቡት፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፳፪–፳፬ (ት. እና ቃ. ፲፯፡፲፪)።

የኤፍሬም በትር። ኤፍሬም—የዮሴፍ ወይም የኤፍሬም በትር *ተመልከቱ*

የእምነት አንቀጾች። *ደግሞም ስሚዝ፣ ጆሴፍ ዳግማዊ፣ የታላቅ ዋጋ ዕንቁ ተመልከቱ*

የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስትያን አባላት የሚደግፏቸው አስራ ሶስት የእ ምነት ነጥቦች።

ጆሴፍ ስሚዝ መጀመሪያ የጻፋቸው የቤተክርስ ትያኗ አባላት ምን እንደሚያምኑ ለማወቅ ለጠየቀው ለ*Chicago Democrat* [ቺካጎ ዴሞክራት ጋዜጣ] አዘጋጂ ለሆነው ጆን ዋንትዎርዝ በመመለስ በጻፈው ደብዳቤ ውስጥ ነው። ደብዳቤው የወንትወርዝ ደብ ዳቤ ተብሎ ታወቀ እና ከመጀመሪያ ጊዜ በ*Times and Seasons* [በጊዜዎች እና በዘመናት] ውስጥ በመጋቢት ፲፰፤፱፯፪ (እ.አ.አ.) ታትሞ ነበር። በጥቅ ምት ፲ ፲፰፤፱ (እ.አ.አ.)፣ የእምነት አንቀጾች በቤ ተክርስትያኗ አባላት ድምፅ መስጠት እንደ ቅዱሣት መጻህፍት በስነስርአታዊ ተቀባይ ሆነ እና በታላቅ ዋጋ ዕንቁ ውስጥም ተጨመረ።

የእስራኤል ልጆች። *እስራኤል ተመልከቱ*

የእስራኤል መሰብሰብ። *እስራኤል—የእስራኤል መሰብሰብ ተመልከቱ*

የእስራኤል መበተን። *እስራኤል—የተበተኑት እስራኤል ተመልከቱ*

የእስራኤል ቅዱስ። *ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልከቱ*

የእስራኤል ቤት። *እስራኤል ተመልከቱ*

የእስራኤል አስራ ሁለት ጎሳዎች። *እስራኤል—የእስራኤል አስራ ሁለት ጎሳዎች ተመልከቱ*

የእውነተኛ ቤተክርስቲያን ምልክቶች። *ደግሞም ምልክት፤ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን፤ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ተመልከቱ*

በእግዚአብሔር ተቀባይነትን እንዳገኘ የሚያሳይ እና ጌታ ልጆቹ የበረከቱን ሙላት እንዲያገኙ የመሰ ረተው ቤተክርስቲያን ትምህርቶችና ስራዎች። የእ ውነተኛ ቤተክርስቲያን አንዳንድ ምልክቶች የሚ ቀጥሉት ናቸው፥

የአምላክ ትክክለኛ እውቀት፣ እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፣ ዘፍጥ. ፩፡፳፯–፳፯። ጌታ ፊት ለፊት ከሙሴ ጋር ተነጋገረ፣ ዘፀአ. ፴፫፡፲፩።

የዘለአለማዊ አባት እግዚአብሔርንና ኢየሱስ ክርስቶስን ማወቅ የዘላለም ሕይወት ነው፣ ዮሐ. ፲፯፡፫።

አብና ወልድ የስጋና አጥንቶች ሰውነቶች አላ ቸው፣ ት. እና ቃ. ፻፴፡፳፪–፳፫።

አብና ወልድ በጆሴፍ ስሚዝ ታዩ፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፲፭–፳። በዘለአለማዊው አብ፣ እግዚአብሔር እናምናለን፣ እ.አ. ፩፡፩።

ቀዳሚ መሰረታዊ መርሆች እና ስነስርዓቶች፣ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር፣ ዮሐ. ፫፡፫–፭። ንስሐ ግቡ፥ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠ መቁ፣ የሐዋ. ፪፡፴፰። በዚያን ጊዜ እጃቸውን ጫኑ ባቸው መንፈስ ቅዱስንም ተቀበሉ፣ የሐዋ. ፰፡፲፭–

፲፯። በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ፣ ገላ. ፫፥፳፮–፳፯።
ንስሀ ግቡ፣ እናም በውዱ ልጄ ስም ተጠመቁ፣ ፪ ኔፊ ፴፩፥፲፩–፳፩።
ያመኑት ተጠመቁ እናም መንፈስ ቅዱስን እጆችን በመጫን ተቀበሉ፣ ት. እና ቃ. ፸፮፥፶–፶፫።
ለመጠመቅ እና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ለመስጠት ትክክለኛው ክህነት ያስፈልጋል፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፸–፸፪። የወንጌሉ ቀዳሚ መሰረታዊ መርሆችና ስነስርዓቶች ተገልጸዋል፣ እ.አ. ፩፥፬።

ራዕይ፣ ራዕይ ባይኖር ሕዝብ መረን ይሆናል፣ ምሳ. ፳፱፥፲፰። እግዚአብሔር ምሥጢሩን ለነቢያት ይነገራል፣ ዓሞ. ፫፥፯።
ቤትክርስቲያኗ በራዕይ አለት ላይ ተገንብታለች፣ ማቴ. ፲፮፥፲፯–፲፰ (ት. እና ቃ. ፴፫፥፲፫)።
ጌታ ከእንግዲህ በራዕይ አይሰራም ለሚል ወዮለት፣ ፫ ኔፊ ፳፱፥፮።
ራዕያትና ትእዛዛት የሚመጡት በተመደበው ብቻ ነው፣ ት. እና ቃ. ፵፫፥፪–፯።
እግዚአብሔር በገለጸው ሁሉ እናምናለን፣ እ.አ. ፩፥፱።

ነቢያት፣ በቤክርስቲያኗ በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ተጸንሳለች፣ ኤፌ. ፪፥፲፱–፳። ሐዋሪያትና ነቢያት ለቤተክርስቲያኗ አስፈላጊ ናቸው፣ ኤፌ. ፬፥፲፩–፲፮።
ጆሴፍ ስሚዝ ባለ ራዕይ፣ ነቢይ፣ እና ሐዋሪያ እንዲሆን ተጠራ፣ ት. እና ቃ. ፳፩፥፩–፫።
በነቢያት እናምናለን፣ እ.አ. ፩፥፮።

ስልጣን፣ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ሀይልና ስልጣን ሰጣቸው፣ ሉቃ. ፱፥፩–፪ (ዮሐ. ፲፭፥፲፮)።
የሔለመን ልጅ ኔፊ ከእግዚአብሔር ታላቅ ስልጣን ነበረው፣ ሔለ. ፲፩፥፲፰ (፫ ኔፊ ፯፥፲፯)።
ነቢያት ለቤትክርስቲያኗ ትእዛዛትን ይቀበሉ፣ ት. እና ቃ. ፳፩፥፬–፭። ስልጣን ባለው ካልተሾም በስተቀር ማንም ወንጌልን መስበክ ወይም ቤተክርስቲያኗን መገንባት አይችልም፣ ት. እና ቃ. ፵፪፥፲፩። ሽማግሌዎች ወንጌልን በስልጣን በመስራት ይስበኩ፣ ት. እና ቃ. ፳፰፥፰።
የሚሰብክ ወይም ለእግዚአብሔር የሚያገለግል ማንም ሰው ስልጣን ባለው ሰው በኩል በእግዚአብሔር መጠራት አለበት፣ እ.አ. ፩፥፭።

ተጨማሪ ቅዱሣት መጻህፍት ይመጣሉ፣ የይሁድ በትር እና የዮሴፍ በትር ይጋጠማሉ፣ ሕዝ. ፴፯፥፲፭–፳።
የኋለኛው ቀን ቅዱሳት መጻህፍት መምጣት ቀድሞ ተነግሮ ነበር፣ ፩ ኔፊ ፲፫፥፴፰–፵፩።
እግዚአብሔር ታላቅና አስፈላጊ ነገሮች ወደፊት እንደሚገልፅ እናምናለን፣ እ.አ. ፩፥፱።

የቤተክርስቲያን ድርጅት፣ በቤክርስቲያኗ በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ተጸንሳለች፣ ኤፌ. ፪፥፲፱–፳። ሐዋሪያትና ነቢያት ለቤተክርስቲያኗ አስፈላጊ ናቸው፣ ኤፌ. ፬፥፲፩–፲፮። ክርስቶስ የቤተክርስቲያን ራስ ነው፣ ኤፌ. ፭፥፳፫።
የክርስቶስ ቤተክርስቲያን በስሙ መጠራት አለባት፣ ፫ ኔፊ ፳፯፥፰።
በድሮው ቤተክርስቲያን እንደነበረው አንድ አይነት ድርጅት እናምናለን፣ እ.አ. ፩፥፮።

የሚስዮን ስራ፣ እንግዲህ ሂዱና፣ እናም አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ፣ ማቴ. ፳፰፥፲፱–፳። ሰብዓዎች ወንጌልን እንዲሰብኩ ተጠሩ፣ ሉቃ. ፲፥፩።
ደህንነት ለሁሉም ፍጡር መታወጅ እንደሚገባው ፍላጎት ነበራቸው፣ ሞዛያ ፳፰፥፫።
ሽማግሌዎች ይሂዱ፣ ሁለት በሁለትም ወንጌሉን ይስበኩ፣ ት. እና ቃ. ፷፪፥፮። ወንጌሉ ለሁሉም ፍጥረቶች መሰበክ አለበት፣ ት. እና ቃ. ፶፰፥፷፬።

መንፈሳዊ ስጦታ፣ በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር፣ የሐዋ. ፪፥፬። ሽማግሌዎች የታመሙትን ይፈውሱ፣ ያዕ. ፭፥፲፬።
የእግዚአብሔርን ስጦታ አትካድ፣ ሞሮኒ ፲፥፰።
መንፈሳዊ ስጦታዎች ተዘርዝረዋል፣ ት. እና ቃ. ፵፮፥፲፫–፳፮ (፩ ቆሮ. ፲፪፥፩–፲፩፤ ሞሮኒ ፲፥፱–፲፰)።

ቤተመቅደሶች፣ የዘላለምም ቃል ኪዳን እሰራለሁ፣ እናም መቅደሴንም ለዘላለም በመካከላቸው አኖራለሁ፣ ሕዝ. ፴፯፥፳፮–፳፯። ጌታ በድንገት ወደ መቅደሱ ይመጣል፣ ሚል. ፫፥፩።
ኔፊ ቤተመቅደስ ሰራ፣ ፪ ኔፊ ፭፥፲፮።
ቅዱሳን የጌታን ቤተ ባለመገንባታቸው ተገሰጹ፣ ት. እና ቃ. ፺፭ (ት. እና ቃ. ፹፰፥፻፲፱)። የጌታ ህዝቦች ቅዱስ ስነስርዓቶችን ለማከናወን ሁልጊዜም ቤተመቅደሶች ይገነባሉ፣ ት. እና ቃ. ፻፳፬፥፴፱–፵፬። ቤተመቅደስን መገንባትና ስነስርዓቶችን ማከናወን የኋለኛው ቀን ታላቅ ስራ ክፍሎች ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፻፴፰፥፶፫–፶፬።

የእግዚአብሔር ልጅ። ኢየሱስ ክርስቶስ፤ እግዚአብሔር፣ አምላክ *ተመልከቱ*

የእግዚአብሔር ልጆች። ሰው፣ ሰዎች፤ የእግዚአብሔር ወንድ እና ሴት ልጆች *ተመልከቱ*

የእግዚአብሔር መንግስት ወይም መንግስተ ሰማያት። *ደግሞም* የሰለስቲያል ክብር፤ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን *ተመልከቱ*

የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን በምድር የምትገኘው የእግዚአብሔር መንግስት ናት (ት. እና ቃ. ፷፭)። የቤተክርስቲያኗም አላማ አባሏን በሰለስቲያል መንግስት ወይም በመንግስተ ሰማያት ውስጥ በዘለአለም ለመኖር ለማዘ

ጋጀት ነው። ነገር ግን፣ ቅዱሣት መጻህፍት አንዳ ንዴ ቤተክርስቲያኗን እንደ መንግስተ ሰማያት ይጠ ሯታል፣ ይህም ቤተክርስቲያኗ በምድር የምትገኝ መንግስተ ሰማያት ናት ማለት ነው።

የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በምድር የምትገኝ የእግዚአብሔር መን ግስት ናት፣ ነገር ግን ይህች በዚህ ጊዜ በመንፈሳዊ መንግስት የተገደበች ናት። በአንድ ሺህ አመት፣ የእግዚአብሔር መንግስት የፖለቲካና የመንፈስ መንግስት ትሆናለች።

እግዚአብሔር ለዘላለም ይነግሣል፣ መዝ. ፲፡፲፯ (መዝ. ፲፩፡፪)። የሰማይ አምላክ ለዘላለም የማይፈ ርስ መንግሥት ያስነሣል ለዘላለምም ትቆማለች፣ ዳን. ፪፡፵፬ (ት. እና ቃ. ፲፵፯፡፵፪)።

መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ፣ ማቴ. ፫፡፪ (ማቴ. ፬፡፲፯)። መንግሥትህ ትምጣ፤ ፈቃ ድህ በምድር ትሁን፣ ማቴ. ፮፡፲። አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ፈልጉ፣ ማቴ. ፮፡፴፫ (፫ ኔፊ ፲፫፡፴፫)። የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈ ቻዎች እሰጥሃለሁ፣ ማቴ. ፲፮፡፲፱። ኑ፣ የተዘጋጀ ላችሁን መንግሥት ውረሱ፣ ማቴ. ፳፭፡፴፬። በአ ባቴ መንግሥት ከእናንተ ጋር ከዚህ ከወይን ፍሬ አዲሱን እስከምጠጣ፣ ማቴ. ፳፮፡፳፯–፳፱። ነቢ ያትን ሁሉ በእግዚአብሔር መንግሥት ታያላችሁ፣ ሉቃ. ፲፫፡፳፰። ዓመፀኞች የእግዚአብሔርን መን ግሥት አይወርሱም፣ ፩ ቆሮ. ፮፡፱። ሥጋና ደም የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርሱ አይችሉም፣ ፩ ቆሮ. ፲፭፡፶።

ሀብትን ከመፈለጋችሁ በፊት፣ የእግዚአብሔ ርን መንግስት ፈልጉ፣ ያዕቆ. ፪፡፲፰። ማንኛውም የረከሰ ነገር መንግስተ ሰማያትን ሊወርስ አይች ልም፣ አልማ ፲፩፡፴፯።

ከእነሱ ጋር በአባቴ መንግስት አብረህ ታርፍ ዘንድ፣ ት. እና ቃ. ፲፭፡፮። መንግስተ ሰማይ፣ ወይም የቤተክርስቲያኗ ቁልፎች ለእናንተ ተሰጥ ታለች፣ ት. እና ቃ. ፵፪፡፶፬ (ት. እና ቃ. ፶፭፡፪)። መንግስተ ሰማያት እንዲመጣም፣ እግዚአብሔር መንግስት ወደፊት ይሄድ፣ ት. እና ቃ. ፶፭፡፭–፮። የመንግስት ቁልፎች ከእንተ በምንም አይወ ሰድብህም፣ ት. እና ቃ. ፶፡፫። እንደ ትንሽ ልጅ የሚቀበልህም፣ መንግስቴን ይቀበላል፣ ት. እና ቃ. ፶፬፡፫። በመጨረሻ ቀናትም በዚህ፣ እንዲሁም በየ ኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክር ስቲያን፣ ስም ነው ቤተክርስቲያኔ የምትጠራው፣ ት. እና ቃ. ፲፲፭፡፬። ሰማያት ተከፈቱልን፣ እና የእግዚአብሔርን ሰለስቲያል መንግስትን አየሁ፣ ት. እና ቃ. ፲፳፯፡፭–፴።

የእግዚአብሔር ሚስጥሮች

የእግዚአብሔር ሚስጥሮች በራዕይ ብቻ የሚ ታወቁ መንፈሳዊ እውነቶች ናቸው። እግዚአብ ሔር ሚስጥሮቹን ለወንጌሉ ታዛዥ ለሚሆኑት ይገ ልጻል። የእግዚአብሔር አንዳንድ ሚስጥሮች ገና አልተገለጹም።

ለእናንተ የመንግሥተ ሰማያትን ምሥጢር ማወቅ ተሰጥቶአችኋል፣ ማቴ. ፲፫፡፲፩። ምሥጢርንም ሁሉ ባውቅ፥ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ፣ ፩ ቆሮ. ፲፫፡፪።

ኔፊ የእግዚአብሔርን ሚስጥር ታላቅ ዕውቀት ነበረው፣ ፩ ኔፊ ፩፡፩። ለብዙዎች የእግዚአብሔ ርን ሚስጥር እንዲያውቁ ተሰጥቷቸዋል፣ አልማ ፲፪፡፱። ለእንደእነዚህ ዓይነቶቹ የእግዚአብሔ ርን ሚስጥር እንዲያውቁ ይሰጣቸዋል፣ አልማ ፳፯፡፲፡ ፳፪፡፰። እነዚህ ሚስጥሮች ሙሉ በሙሉ ለእኔ አልታወቁኝም፣ አልማ ፴፯፡፲፩። እግዚአብሔር እራሱ ካልሆነ በቀር ማንም የማያውቃቸው ብዙ በአምላክ የተደበቁ ሚስጥሮች አሉ፣ አልማ ፴፡፲።

የአምላክነት ሚስጥር እንዴት ታላቅ ነው፣ ት. እና ቃ. ፲፱፡፲። ከጠየቃችሁ፣ ራዕይ ትቀበ ላላችሁ፣ እናም የመንግስት ሚስጥራትን ታው ቃላችሁ፣ ት. እና ቃ. ፵፪፡፳፭፣ ፳፮ (፩ ቆሮ. ፪፡፯፣ ፲፩–፲፪)። ትእዛዛቴን ለሚጠብቀው የመ ንግስቴን ሚስጥሮች እሰጠዋለሁ፣ ት. እና ቃ. ፳፫፡፳፫። ለእነርሱም ሁሉንም ሚስጥሮች እገልጻ ለሁ፣ ት. እና ቃ. ፫፲፯፡፯። ታላቅ የክህነት የሚስጥር ቁልፎችን ይሏል፣ ት. እና ቃ. ፲፲፡፲፱። ጌታ በሚ መጣበት ጊዜ ማንም ሰው የማያውቃቸውን የተደ በቁ ነገሮችን ይገልጻል፣ ት. እና ቃ. ፲፭፡፴፪–፴፫። የመልከ ጼዴቅ ክህነት የሰማይ መንግስትን ሚስጥ ሮች ለመቀበል ልዩ መብት ይኑረው፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፲፱።

የእግዚአብሔር ቃል

ደግምም ራዕይ፣ ቅዱሳት መጻህፍት፣ የእግዚአብሔር ትእዛዛት ተመለከቱ

መመሪያዎች፣ ትእዛዛት፣ ወይም ከእግዚአብ ሔር የመጣ መልእክት የእግዚአብሔር ልጆች ቃሉን በመንፈስ በኩል በቀጥታ ራዕይ ወይም በተመረጡት አገልጋዮቹ መቀበል ይችላሉ (ት. እና ቃ. ፩፡፴፯)።

ሰውም ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ነገር ሁሉ በሕይወት ይኖራል፣ ዘዳግ. ፰፡፫ (ማቴ. ፬፡፬፣ ት. እና ቃ. ፴፬፡፴–፴፭)። ሕግህ ለእግሬ መብ ራት፥ ለመንገዴ ብርሃን ነው፣ መዝ. ፻፲፱፡፲፭።

በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ የእግዚአብ ሔርንም ቃል በግልጥ ተናገሩ፣ የሐዋ. ፬፡፴፩–፴፫።

የብረት በትር የእግዚአብሔር ቃል ነው፣ ፩ ኔፊ ፲፩፡፳፭ (፩ ኔፊ ፲፫፡፳፫–፳፭)። እናንተ ደንገዝ ችኋል፣ ስለዚህ ቃሉ ሊሰማችሁ አልቻለም፣ ፩ ኔፊ ፲፯፡፶፭–፶፮። የእግዚአብሔርን ቃል ለማይቀ በል ለዚያ ሰው ወሮለት፣ ፪ ኔፊ ፳፯፡፲፡ (፪ ኔፊ

ፀ፰፡፡ ፀ፱፣ ኤተር ፬፡ ፰)። የክርስቶስን ቃል በመ መገብ፣ እስከመጨረሻው በመፅናት ቀጥሉ፣ ፪ ኔፊ ፴፩፡ ፀ (፪ ኔፊ ፴፪፡ ፫)። ባለማመናቸው የእግዚ አብሔርን ቃል ሊረዱት አልቻሉም ነበር፣ ሞዛያ ፀ፯፡ ፫ (አልማ ፲፪፡ ፲)። የእግዚአብሔርን ቃል ያውቁ ዘንድ ቅዱሳን መጻሕፍትን በትጋት አጥን ተዋል፣ አልማ ፲፯፡ ፪። የእግዚአብሔር ቃል በጎ ነት ሞክሩ፣ አልማ ፴፩፡ ፭። አልማ የእግዚአብሔ ርን ቃል ከዘር ጋር አነጻጸረ፣ አልማ ፴፪፡ ፀ፰–፴፫።

በመንፈስ ቅዱስ ሲነሳሱ የሚናገሩት ማንኛውም ነገር ቅዱሣት መጻህፍት ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፀ፰፡ ፀ። ከእግዚአብሔር አፍ ከሚመጣው እያን ዳንድ ቃልም ትኖራላችሁ፣ ት. እና ቃ. ፴፬፡ ፴፭–፴፮።

ቃላቶቼን እንደሀብት የሚያከማቸው ማንም አይ ታለልም፣ ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፡ ፴፯።

የእግዚአብሔር በግ

ደግሞም ኢየሱስ ክርስቶስ፣ የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ፣ ፋሲካ ተመልከቱ

ኢየሱስን ለእኛ ጥቅም እንደሚሰዋው የሚያመ ለክተው ለአዳኝ የተሰጠ ስም።

ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት መጥቷል፣ ኢሳ. ፶፫፡ ፯ (ሞዛያ ፲፬፡ ፯)።

እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአ ብሔር በግ፣ ዮሐ. ፩፡ ፀ፱ (አልማ ፯፡ ፲፬)። እድፍ እንደ ሌለው እንደ በግ ደም በክቡር የክርስቶስ ደም እንደ ተዋጃችሁ ታውቃላችሁ፣ ፩ ጴጥ. ፩፡ ፲፰–ፀ። የታረደው በግ ክብር ሊቀበል ይገባዋል፣ ራዕ. ፭፡ ፲፪። በበጉ ደም የተነሣ በሰይጣን ላይ ድል ነሳን፣ ራዕ. ፲፪፡ ፲፩።

እነዚህ በእርሱ ባላቸው እምነት ምክንያት በበጉ ደም ነፅተዋል፣ ፩ ኔፊ ፲፪፡ ፲፩። የእግዚአብሔርም በግ የዘለአለማዊው አባት ልጅና የአለም አዳኝ ነው፣ ፩ ኔፊ ፲፫፡ ፴ (፩ ኔፊ ፲፩፡ ፀፀ)። ምናልባት በመ ጨረሻው እና በዚያ በታላቁ ቀን እንከን የሌላችሁ፣ ንፁህ፣ መልካም፣ እናም በበጉ ደም የፀዳችሁ ሆና ችሁ ትገኙ ዘንድ ወደ አብ በኢየሱስ ስም በኃይል ጩሁ፣ ሞር. ፱፡ ፮ (ራዕ. ፯፡ ፲፡ አልማ ፴፡ ፴፯)።

፴፯ የሰው ልጅ ከምድር መሰረት ጀምሮም የተ ገደለው በግ ነው፣ ሙሴ ፯፡ ፴፯።

የእግዚአብሔር ትእዛዛት

ደግሞም ህግ፣ ታዛዥነት፣ ታዛዥ፣ መታዘዝ፣ ኃጢያት፣ አስሩ ቃላት፣ የእግዚአብሔር ቃል ተመልከቱ።

በግል ወይም ለሁሉም የተሰጡ ህግጋት እና እግ ዚአብሔር በሰው የሚፈልጋቸው ነገሮች። ትእዛዛ ትን መጠበቅ ለታዛዦች የጌታን በረከቶች ያመጥል (ት. እና ቃ. ፲፴፡ ፀ፩)።

ኖኅም እግዚአብሔር እንዳዘዘው ሁሉ እንዲሁ አደረገ፣ ዘፍጥ. ፮፡ ፀ፪። በሥርዓቴ ብትሄዱ፡ ትእዛዛቴንም ብትጠብቁ ብታደርጉትም፣ ዘሌዋ. ፳፮፡ ፫። ትእዛዜን ጠብቅ በሕይወትም ትኖራለህ፣ ምሳ. ፬፡ ፬ (ምሳ. ፯፡ ፪)።

ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ፣ ዮሐ. ፲፬፡ ፲፭ (ት. እና ቃ. ፴፪፡ ፀ፱)። ትእዛዙንም የምንጠብቅ ስለሆንን የምንለምነውን ሁሉ ከእርሱ እናገኛለን፣ ፩ ዮሐ. ፫፡ ፀ፪። ትእዛዛቱም ከባዶች አይደሉም፣ ፩ ዮሐ. ፭፡ ፫።

ትዕዛዝ በመጠበቅ ጠንካራ፣ ፅኑና፣ የማትነቃነቅ ሁኑ፣ ፩ ኔፊ ፪፡ ፲። ጌታ ለማሟላት መንገድ ካላዘ ጋጀ በቀር ትእዛዛት አይሰጥም፣ ፩ ኔፊ ፫፡ ፯። በእ ግዚአብሔር ጥብቅ ትዕዛዝ መሰረት ማድረግ አለ ብኝ፣ ያዕቆ. ፪፡ ፲። ትእዛዛቴን እስከጠበክ ድረስ በምድሯ ትበለፅጋለህ፣ ጄረም ፩፡ ፱ (አልማ ፱፡ ፲፫፣ ፶፡ ፀ)። በወጣትነትህ ትእዛዛትን ለማክበር ተማር፣ አልማ ፴፯፡ ፴፩።

እነዚህ ትእዛዛት ከ እኔ ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፩፡ ፀ፩። ትእዛዛትን መርምሩ፣ ት. እና ቃ. ፩፡ ፴፯። ትእዛዛትን የማይጠብቁ ሊድኑ አይች ሉም፣ ት. እና ቃ. ፲፰፡ ፴፯ (ት. እና ቃ. ፀ፩፡ ፲፩፣ ፶፯፡ ፪)። ትእዛዛት የሚሰጡት የጌታን ፈቃድ እንድ ንረድ ነው፣ ት. እና ቃ. ፀ፱፡ ፴፩። ትእዛዛት የሚ ሰጡት የጌታ ፈቃድ እንዲገባን ነው፣ ት. እና ቃ. ፴፪፡ ፰።

እግዚአብሔር ስላዘዘኝ እንጂ፣ ለምን እንደሆነ አላውቅም፣ ሙሴ ፩፡ ፯። እና ጌታ አምላክ የሚ ያዛቸውን ማንኛቸውንም ነገሮች ሁሉ እንደሚያ ደርጉ ለማየት፣ በዚህ እንፈትናቸዋለን፣ አብር. ፫፡ ፀ፩።

የእግዚአብሔር ወንድ እና ሴት ልጆች

ደግሞም መወለድ፣ ሰው፣ ሰዎች፣ የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ፣ የክርስቶስ ልጆች፣ ዳግመኛ መወለድን፣ ከእግዚአብሔር መወለድ ተመልከቱ

ቅዱሣት መጻህፍት እነዚህን አባባሎች በሁለት መንገድ ተጠቅመውባቸዋል። በአንድ አስተያየት፣ ሁላችንም የሰማይ አባታችን የመንፈስ ልጆች ነን። በሌላ አስተያየት፣ የእግዚአብሔር ወንድ እና ሴት ልጆች በክርስቶስ የኃጢያት ክፍያ በኩል እንደገና የተወለዱት ናቸው።

የአብ የመንፈስ ልጆች፣ አማልክት ናችሁ፡ ሁላ ችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ፣ መዝ. ፹፪፡ ፮።

የእግዚአብሔር ዘመዶች ነን፣ የሐዋ. ፲፯፡ ፀ፱። ለመናፍስት አባት አብልጠን ልንገዛ ይገባናል፣ ዕብ. ፲፪፡ ፱።

የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ፣ ሙሴ ፩፡ ፲፫።

በኃጢያት ክፍያ በኩል እንደገና የተወለዱ

ልጆች፣ ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፣ ዮሐ. ፩፥፲፪ (ሮሜ ፰፥፲፬፣ ፫ ኔፊ ፱፥፲፯፣ ት. እና ቃ. ፲፩፥፴)። አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፣ ፩ ዮሐ. ፫፥፩–፪።

የክርስቶስ ልጆች፣ ወንዶች እና ሴት ልጆቹ፣ ተብላችሁ ትጠራላችሁ፣ **ሞዛያ** ፭፥፯። ሁሉም ሰው፣ ወንዶችና ሴቶች፣ በድጋሚ መወለድ ይገባቸዋል፣ **ሞዛያ** ፳፯፥፳፭። እነርሱም ወንድና ሴት ልጆቼም ይሆናሉ፣ **ኤተር** ፫፥፲፬። በእርግጥ እናንተ የክርስቶስ ልጆች ትሆናላችሁ፣ **ሞሮኒ** ፯፥፲፱።

ወንጌሌን የሚቀበሉ ሁሉ በመንግስቴ ወንድ ልጆች እና ሴት ልጆች ናቸው፣ **ት. እና ቃ.** ፳፭፥፩። እነርሱ አማልክቶች፣ እንዲሁም የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው፣ **ት. እና ቃ.** ፸፮፥፶፰።

እንደዚህ ሁሉም የእኔ ልጆች መሆን ይችላሉ፣ **ሙሴ** ፮፥፰፰። ብዙዎችም አመኑና የእግዚአብሔር ልጆች ሆኑ፣ **ሙሴ** ፯፥፩።

የከርትላንድ ቤተመቅደስ፣ ኦሀዮ (ዮ.ኤስ.ኤ.)

በዚህ ዘመን በቤተክርስቲያኗ የተገነባ የመጀመሪያ ቤተመቅደስ። ቅዱሳን በከርትላንድ ውስጥ፣ በጌታ ትእዛዝ መሰረት ገነቡት (ት. እና ቃ. ፺፬፥፫–፱)። የቦታው አንድ አላማም ብቁ የሆኑ የቤተክርስቲያኗ አባላት መንፈሳዊ ሀይል፣ ስልጣን፣ እና መብራራትን ለመቀበል እንዲችሉ ነበር (ት. እና ቃ. ፻፱–፻፲)። በመጋቢት ፳፯፣ ፲፰፻፴፮ (እ.አ.አ.) ተመረቀ፤ የመመረቂያው ጸሎት የተሰጠውም በራዕይ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል ነበር (ት. እና ቃ. ፻፱)። በእዚህ ቤተመቅደስ ውስጥ ጌታ ብዙ አስፈላጊ ራዕዮችን ሰጠ እናም አስፈላጊ የሆኑትን የክህነት ቁልፎችንም ዳግሞ መለሰ (ት. እና ቃ. ፻፲፤ ፻፴፯)። በዛሬ ቤተመቅደሶች ውስጥ የሚሰጡትን ሙሉ የመንፈስ ስጦታዎችን ለመስጠት አልተጠቀሙበትም ነበር።

የኪዳን ታቦት። *ደግሞም ታቦት ተመልከቱ*

ደግሞም የያህዌህ ታቦት እና የምስክር ታቦት ተብሎ የሚታወቀው የኪዳን ታቦት በወርቅ የተሸፈነ ከእንጨት የተሰራ የአራት ማዕዘን አይነት ሰንዱቅ ወይም ሳጥን ነበር። ከእስራኤላውያን የሀይማኖት ምልክቶች የጥንት እና ታላቅ ቅድስና ያለው ነበር። መደረቢያውን የሚሰራው የስርየት መክደኛው እንደ ያህዌህ የምድር መኖሪያ ቦታ ይታሰብበት ነበር (ዘፀአ. ፳፭፥፳፪)። ቤተመቅደሱ በተፈጸመበት ጊዜ፣ የኪዳን ታቦት፣ በአካል ከሁሉም በላይ ቅዱስ በሆነው ቦታ፣ በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ተቀመጠ (፩ ነገሥ. ፰፥፩–፰)።

ሙሴ ታቦትን በእግዚአብሔር ትእዛዝ ሰራ፣ **ዘፀአ.** ፳፭። የሌዊ ልጆች ታቦቱን እንዲጠብቁ ሀላፊነት ተሰጥቷቸው ነበር፣ **ዘኁል.** ፫፥፲፭፣ ፴፩። የኪዳን ታቦት ቀድሞአቸው ሄደ፣ **ዘኁል.** ፲፥፴፫። ይህን የሕግ መጽሐፍ ውሰዱ፣ በኪዳን ታቦት ውስጥም ጨምሩት፣ **ዘዳግ.** ፴፩፥፳፬–፳፮። የዮርዳኖስ ውሀ በኪዳን ታቦት ፊት ተቋረጠ፣ **ኢያ.** ፫፥፲፫–፲፯፤ ፬፥፩–፯። ካህናት ኢያሪኮን ለማሸነፍ የኪዳን ታቦትን ወሰዱ፣ **ኢያ.** ፮፥፮–፳። ፍልስጥኤማውያንም የእግዚአብሔርን ታቦት ወሰዱ፣ **፩ ሳሙ.** ፭። ጌታ የአቢዳራን ቤት በእግዚአብሔር ታቦት ምክንያት ባረከው፣ **፪ ሳሙ.** ፮፥፲፩–፲፪። ዖዛ ታዛዥ ባላመሆን ታቦቱን ለመደገፍ ስለሞከረ በጌታ ተቀሠፈ፣ **፩ ዜና** ፲፫፥፱–፲፪ (ት. እና ቃ. ፹፭፥፰)። የኪዳን ታቦትን ታመጡ ዘንድ፣ የአምላክን የእግዚአብሔርን መቅደስ ሥሩ፣ **፩ ዜና** ፳፪፥፲፱።

የኪዳን ታቦት በውስጡ የያዘው ተገልጸዋል፣ **ዕብ.** ፱፥፬።

የካህን ተንኮል

ገንዘብ እና ምስጋናን ከአለም ለማግኘት እራሳቸውን እንደ አለም ብርሀን ከፍ የሚያደርጉ እና የሚሰብኩ ሰዎች፤ የፅዮንን ደህንነት አይፈልጉም (፪ ኔፊ ፳፮፥፳፱)።

የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ በመጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን፣ **፩ ጴጥ.** ፭፥፪።

ሀብትን ለማግኘት የተመሰረቱት ቤተክርስቲያኖች ሁሉ መዋረድ ያለባቸው ናቸው፣ **፩ ኔፊ** ፳፪፥፳፫ (ሞር. ፰፥፴፪–፵፩)። በኃጢያትና በካህናት ተንኮል የተነሳ ኢየሱስ ይሰቀላል፣ **፪ ኔፊ** ፲፥፭። በየካህን ተንኮል በህዝቡ መካከል በግዴታ የሚደረግ ቢሆን ይህም አጠቃላይ ጥፋታቸውን ያስከትላል፣ **አልማ** ፩፥፲፪። አህዛብ በሁሉም አይነት ካህናት ተንኮል ይሞላሉ፣ **፫ ኔፊ** ፲፮፥፲።

የካርቴጅ እስር ቤት (ዩ.ኤስ.ኤ.)። *ደግሞም ስሚዝ፣ ሀይረም፤ ስሚዝ፣ ጆሴፍ ዳግማዊ ተመልከቱ*

ጆሴፍ እና ሀይረም ስሚዝ በሰኔ ፳፯፣ ፲፰፻፵፬ (እ.አ.አ.) በካርቴጅ፣ ኢለኖይ ዮናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ እስር ቤት ውስጥ ተገድለው ነበር (ት. እና ቃ. ፻፴፭)።

የክህነት መህላ እና ቃል ኪዳን። *ደግሞም መህላ፤ ቃል ኪዳን፤ ክህነት ተመልከቱ*

መህላ እውነትነት እና ለሰው የተገባ ቃል ኪዳን ታማኝ ለመሆን በመማል የሚረጋገጥበት ነው። ቃል ኪዳን የሁለት ቡድኖች ክብር ቃል ኪዳን ነው። የአሮናዊ ክህነት የሚቀበሉት በቃል ኪዳን ብቻ ነው። የመልከ ጼዴቅ የክህነት ባለስልጣኖች ክህነትን የሚቀበሉት በቃል በማይነገር መህላና በቃል ኪዳን ነው። የክህነት ባለስልጣናት ታማኝ ናቸው እናም እግዚአብሔር እንደሚመራቸው ጥሪአቸውን ያጎ

ላሉ፣ እርሱም ይባርካቸዋል። እስከመጨረሻ ታማኝ የሆኑት እና እርሱ የሚጠይቀውን ሁሉ የሚያደርጉት አብ ያለውን ሁሉ ይወርሳሉ (ት. እና ቃ. ፹፬፥፴፫–፴፱)።

ጌታ ከአብርሐም ጋር ቃል ገባ፣ እናም አብርሐምም ታዛዥ ሆነ፣ ዘፍጥ. ፲፩፥፲፰፤ ፲፯፥፩፤ ፳፪፥፲፮–፲፰። በሕዝቅኤል ጊዜ ካህናት በጎቹን አላሰማሩም፣ ሕዝ. ፴፬፥፪–፫። በሚልክያስ ጊዜ ካህናት ቃል ኪዳንን አበላሹ፣ ሚል. ፩–፪።

የክህነት ሹመት። *መሾም፣ ሹመት ተመልከቱ*

የክህነት ቁልፎች። *ደግሞም ቀዳሚ አመራር፤ ክህነት፤ ዘመን ተመልከቱ*

ቁልፎች የአመራር መብቶች፣ ወይም የእግዚአብሔርን ክህነት በምድር ላይ እንዲመራ፣ እንዲቆጣጠር፣ እና ገዢ እንዲሆን በእግዚአብሔር ለሰው የተሰጠ ሀይል ነው። ለአመራር ኃላፊነት የተጠሩ የክህነት ባለስልጣኖች ቁልፎችን ከእነርሱ በላይ ስልጣን ካላቸው ይቀበላሉ። የክህነት ባለስልጣኖች ክህነትን ለመጠቀም የሚችሉት ቁልፎችን የያዙት በሚሰጡት መጠን ውስጥ ብቻ ነው። የቤተክርስቲያኗ ፕሬዘደንት በምድር ላይ ሁሉንም የክህነት ቁልፎች ለመያዝና ለመጠቀ የሚችለው የቤተክርስቲያኗ ፕሬዘደንት ብቻ ነው (ት. እና ቃ. ፻፯፥፷፭–፷፯፣ ፺፩–፺፪፤ ፻፴፪፥፯)።

ጴጥሮስ የመንግስትን ቁልፎች ተቀበለ፣ ማቴ. ፲፮፥፲፱።

ሚካኤልን (አዳም) የደህንነትን ቁልፎች በኢየሱስ ክርስቶስ አመራር በኩል ተቀበለ፣ ት. እና ቃ. ፸፰፥፲፮። የመንግስት ቁልፎች ሁልጊዜም ለቀዳሚ አመራር የሚሆን ነው፣ ት. እና ቃ. ፹፩፥፪። የመልከ ጼዴቅ ክህነት የእግዚአብሔር መንግስትን ሚስጥር ቁልፎችን ይዟል፣ ት. እና ቃ. ፹፬፥፲፱። አስራ ሁለቱ ልዩ ቆልፎች ይዘዋል፣ ት. እና ቃ. ፻፯፥፴፭፤ ፻፲፪፥፲፮፣ ፴፪፤ ፻፳፬፥፻፳፰። ጆሴፍ ስሚዝ እና ኦሊቨር ካውደሪ የእስራኤልን መሰብሰብ፣ የአብርሐምን ወንጌል፣ እና የማስተሳሰር ሀይሎችን በሚመለከት ቁልፎች ተቀበሉ፣ ት. እና ቃ. ፻፲፥፲፩–፲፮። ቀዳሚ አመራር እና አስራ ሁለቱ የዘመን ፍጻሜ ቆልፎችን ይዘዋል፣ ት. እና ቃ. ፻፲፪፥፴–፴፬። የክህነት ባለስልጣኖች ቁልፎች ይዘዋል፣ ት. እና ቃ. ፻፳፬፥፻፳፫። ቁልፎች የተሰጠው እውቀቶችን ለማግኘት ይችላል፣ ት. እና ቃ. ፻፳፰፥፲፩።

የአሮናዊ ክህነት የመልእክትን እና የንስሃ ወንጌልን እና የጥምቀት አገልግሎት ቁልፎችን ይዟል፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፷፱ (ት. እና ቃ. ፲፫)።

የክርስቶስ ልጆች። *ደግሞም መወለድ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ የእግዚአብሔር ወንድ እና ሴት ልጆች፤ ዳግመኛ መወለድን፣ ከእግዚአብሔር መወለድ ተመልከቱ*

የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልን የተቀበሉት።

እንደዚህ ሕፃን ራሱን የሚያዋርድ ሁሉ፥ በመንግሥተ ሰማያት የሚበልጥ እርሱ ነው፣ ማቴ. ፲፰፥፩–፬። የብርሃን ልጆች እንድትሆኑ በብርሃኑ እመኑ፣ ዮሐ. ፲፪፥፴፮።

ፍጥረታዊው ሰውነትን ቀይር እናም እንደ ልጅ ሁን፣ ሞዛያ ፫፥፲፱፤ ፳፯፥፳፭–፳፮። በገባችሁት ቃል ኪዳን የተነሳ የክርስቶስ ልጆች ትባላላችሁ፣ ሞዛያ ፭፥፯። መልካም የሆኑትን ሁሉ የምትይዙ ከሆነ፣ እናም ካልኮነናችሁት፣ በእርግጥ እናንተ የክርስቶስ ልጆች ትሆናላችሁ፣ ሞሮኒ ፯፥፲፱።

ለተቀበሉኝ ሁሉ ልጆቼ እንዲሆኑ ኃይልን ሰጠኋቸው፣ ት. እና ቃ. ፴፱፥፬። አትፍሩ፣ ህጻናት፣ የእኔ ናችሁና፣ ት. እና ቃ. ፶፥፵–፵፩።

አንተ በእኔ አንድ ነህ፣ የእግዚአብሔርም ልጅ፣ ሙሴ ፮፥፷፰።

የክርስቶስ ተቃዋሚ። *ደግሞም ዲያብሎስ ተመልከቱ*

የእውነት ወንጌልን የደህንነት አላማ አስመስሎ የሚሰራ እና በግልፅ ወይም በሚስጥር ክርስቶስን የሚቃወም ሰው ወይም ነገር። ገላጩ ዮሐንስ የክርስቶስ ተቃዋሚን እንደ አታላይ ገልጾታል (፩ ዮሐ. ፪፥፲፰–፳፪፤ ፬፥፫–፮፤ ፪ ዮሐ. ፩፥፯)። ታላቁ የክርስቶስ ተቃዋሚ ሉሲፈር ነው፣ ነገር ግን መንፈሳዊ እና ስጋዊ ፍጡር የሆኑ ብዙ ደጋፊዎች አሉት።

አምላክ ከተባለው ሁሉ ላይ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርገው ተቃዋሚ የጥፋት ልጅ፣ ፪ ተሰ. ፪፥፩–፲፪። ከተሰጡት ምልክቶች የተነሣ በምድር የሚኖሩትን ያስታል፣ ራዕ. ፲፫፥፲፫–፲፯።

ሼረም ክርስቶስን ካደ እናም ብዙዎችን አታለለ፣ ያዕቆ. ፯፥፩–፳፫። ኔሆር ሀሰተኛ ትምህርት አስተማረ፣ ቤተክርስቲያንን አቋቋመ፣ የካህን ተንኮልን ጀመረ፣ አልማ ፩፥፪–፲፮። ቆሪሆር፣ በክርስቶስ፣ በኃጢያት ክፍያው እና በትንቢት መንፈስ ተሳለቀ፣ አልማ ፴፥፮–፷።

የክርስቶስ ትምህርት። *ደግሞም ወንጌል፤ የቤዛነት ዕቅድ ተመልከቱ*

የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መሰረታዊ መርሆችና ትምህርቶች።

ትምህርቴ እንደ ዝናብ ትፈስሳለች፣ ዘዳግ. ፴፪፥፪። የሚያጉረመርሙም ትምህርትን ይቀበላሉ፣ ኢሳ. ፳፱፥፳፬።

ሕዝቡ በትምህርቱ ተገረሙ፣ ማቴ. ፯፥፳፰። ትምህርቴስ ከላከኝ ነው እንጂ ከእኔ አይደለም፣ ዮሐ. ፯፥፲፮። ቅዱስ መጻሕፍት ሁሉ ለትምህርትና ይጠቅማል፣ ፪ ጢሞ. ፫፥፲፮።

ይህ የክርስቶስ ትምህርት ነው፣ የአብ ብቸኛ ውና እውነተኛው ትምህርት ነው፣ ፪ ኔፊ ፴፩፡፭ (፪ ኔፊ ፴፪፡፲)። በትምህርቴ ነጥቦችም ምክንያት በመካከላችሁ ፀብ አይኖርም፣ ፫ ኔፊ ፲፩፡፳፭፣ ፴፭፣ ፴፱–፴። ፡

የትምህርቴ ነጥቦች በተመለከተ ሰይጣን የሰዎችን ልብ ለፀብ ያነሣሳል፣ ት. እና ቃ. ፲፡፶፪–፶፫፣ ፶፯። ልጆችን ስለንስሀ መግባት፣ በክርስቶስ እምነት፣ እናም ስለጥምቀትና ስለመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ትምህርት አስተምሯቸው፣ ት. እና ቃ. ፶፫፡፳፫፡፳፭። የመንግስትን ትምህርቶች እርስ በርስ ተማሩ፣ ት. እና ቃ. ፲፫፡፶–፳፯፡፶–፳፯፡፶። የክህነት ትምህርትም በነፍስህ ላይ እንደ ሰማይ ጠል ይንጠባጠባል፣ ት. እና ቃ. ፲፳፭፡፶፭፡፷፭።

የክብር ደረጃዎች። *ደግምም ተረስትሪያል ክብር፣ ቲለስቲያል ክብር፣ የሰለስቲያል ክብር ተመልከቱ*

የሚለያዩ የሰማይ መንግስታት። በመጨረሻው ፍርድ፣ የጥፋት ልጆች ከሆኑት በስተቀር፣ እያን ዳንዱ ሰው በልዩ የክብር መንግስት ውስጥ ዘለአለማዊ መኖሪያ ይወርሳሉ።

ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፣ ዮሐ. ፲፬፡፪ (ኤተር ፲፪፡፴፪)። የፀሐይ ክብር አንድ ነው የጨረቃም ክብር ሌላ ነው የከዋክብትም ክብር ሌላ ነው፣ ፩ ቆሮ. ፲፭፡፴–፴፩። ጳውሎስ እስከ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ ተነጠቀ፣ ፪ ቆሮ. ፲፪፡፪።

ክብር የሌለበትና የዘለአለም ቅጣት የሆነ ቦታ አለ፣ ት. እና ቃ. ፷፯፡፴–፴፣ ፸፫–፸፭። ሶስት የክብር ክፍሎች አሉ፣ ት. እና ቃ. ፷፯፡፶–፸፫፣ ፸፫፡፳–፸፪።

የወሲብ ድርጊቶችን የሚያሳዩ መጻህፍት እና ፊልሞች። *ማመንዘር፣ ንጹህነት፣ ዝሙት መፈጸም ተመልከቱ*

የወርቅ ሰሌዳዎች። *ደግምም መፅሐፈ ሞርሞን፣ ሰሌዳዎች ተመልከቱ*

በወርቅ ሰሌዳዎች ላይ የተጻፈ መዝገብ። በአሜሪካ ክፍለ አህጉር ላይ ስለነበሩ የሁለት ታላቅ ስልጣኔዎች ታሪክ ይነግራል። ጆሴፍ ስሚዝ የእ ነዚህ ሰሌዳዎችን ክፍል ተረጎመ እናም አተመ። ይህ ትርጉም መፅሐፈ ሞርሞን ይባላል። (ለተጨ ማሪ መረጃ፣ በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ ያሉትን “መግቢያን” እና “የነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ ምስክርን” ተመልከቱ።)

የወንጌሉ ቀዳሚ መሰረታዊ መርሆች። *መንፈስ ቅዱስ፣ መጸጸት፣ ንስሀ መግባት፣ እምነት፣ ማመን፣ ጥምቀት፣ መጥመቅ ተመልከቱ*

የወንጌል ዳግም መመለስ። *ደግምም ስሚዝ፣ ጆሴፍ ዳግማዊ፣ ክህደት፣ ወንጌል፣ ዘመን ተመልከቱ*

እግዚአብሔር በምድር ላይ በሰዎች መካከል የወ ንጌሉን እውነት እና ስርዓቶችን እንደገና መመስ ረቱ። የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ከክርስቶስ ሐዋሪ ያት አገልግሎት በኋላ በክህደት በኩል ጠፍቶ ነበር። ያም ክህደት የወንጌሉ ዳግም መመለስን አስፈላጊ አደረገ። በራዕዮች፣ በሚያገለግሉ መላእክቶች፣ እና በምድር ላሉት ሰዎች ራዕይ በመስጠት፣ እግ ዚአብሔር ወንጌልን ዳግም መለሰ። ዳግም መመ ለስ የተጀመረው በጆሴፍ ስሚዝ ነበር (ጆ.ስ.—ታ. ፩፣ ት. እና ቃ. ፲፳፭፡፭–፭፩)፣ እናም እስከ አሁን ድረስ በጌታ ህያው ነቢያት ስራዎች በኩል ቀጥሏል።

የእግዚአብሔር ቤት ተራራ በተራሮች ራስ ላይ ጸንቶ ይቆማል፣ ኢሳ. ፪፡፪ (ሚክ. ፬፡፪፣ ፪ ኔፊ ፲፪፡፪)። እግዚአብሔር ድንቅ ነገርን ተአምራት ንም ያደርጋል፣ ኢሳ. ፭፬፡፲፬ (፪ ኔፊ ፭፭፡፲፯–፲፡፣ ት. እና ቃ. ፬፡፩)። አምላክ ለዘላለም የማይ ፈርስ መንግሥት ያስነሣል፣ ዳን. ፪፡፴፬።

ኤልያስማ አስቀድሞ ይመጣል ሁሉንም ያቀ ናል፣ ማቴ. ፲፯፡፲፩ (ማር. ፱፡፲፪፣ ት. እና ቃ. ፷፯፡፲፬)። ነገር ሁሉ የሚታደስበት ዘመን ይደር ሳል፣ የሐዋ. ፫፡፳፩ (ት. እና ቃ. ፭፯፡፲)። በዘ መን ፍጻሜ ሁሉንም ነገሮች እግዚአብሔር ይጠቀ ልላል፣ ኤፌ. ፩፡፲። የዘላለም ወንጌል ያለው ሌላ መልአክ አየሁ፣ ራዕ. ፲፬፡፯።

የወንጌል ሙላት ወደ አህዛብ ይመጣል፣ ፩ ኔፊ ፲፭፡፲፫–፲፡፡ አይሁድ ወደ እውነተኛው ቤተ ክር ስቲያ ደግመው ይመጣሉ፣ ፪ ኔፊ ፱፡፪። በጓሊኛው ቀን እውነት ትመጣለች፣ ፫ ኔፊ ፲፯፡፯።

የአሮናዊ ክህነትን ለእናንተ እሰጣችኋለሁ፣ ት. እና ቃ. ፲፫ (ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፷፱)። የመንግስቴን ቁልፎች ለመጨረሻ ጊዜ ሰጥቻለሁ፣ ት. እና ቃ. ፭፯፡፯፣ ፲፫–፲፱ (ት. እና ቃ. ፲፭፡፷–፲፱–፳፩)። የእስራኤልን አስራ ሁለት ጎሳዎችን ሰብስብ እናም ሁሉንም ነገሮች በዳግም መልስ፣ ት. እና ቃ. ፷፯፡፱። የዚህ የዘመን ፍጻሜ ቁልፎች ተሰጥተ ዋል፣ ት. እና ቃ. ፲፣፡፲፯ (ት. እና ቃ. ፷፭፡፪)። የክህነት ሀይል የሙሉ ዘመን ፍጻሜ ተሰጥቷል፣ ት. እና ቃ. ፲፣፲፪፡፴።

ሁለት ሰዎች አየሁ፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፲፯። በኤል ያስ እጅ፣ ክህነትን እገልፅልሀለሁ፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፴፯ (ሚል. ፬፡፭–፮)።

የወይራ ዛፍ። *ደግምም እስራኤል፣ ዘይት ተመልከቱ*

በእስራኤል ውስጥ በልምድ የሚገኝ እና በመፅ ሐፍ ቅዱስ ምድሮች ውስጥ አስፈላጊ የእርሻ ጥሬ እቃ የሆነ ዛፍ። የሚያድገውም ለእንጨቱ፣ ለፍ

ሬው፣ እና ለዘይቱ ነበር። በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ እንደ እስራኤል ቤት ምሳሌ የወይራ ዛፍን በብዛት ይጠቀሙበት ነበር።

የእስራኤልን ቤት ልክ ቅርንጫፎቹ እንደወደቁበትና እንደተበተኑት ወይራ ዛፍ ተነፃፀረዋል፣ ፩ ኔፊ ፲፥፲፪ (፩ ኔፊ ፲፭፥፲፪)። ጌታ የእስራኤል ቤትን ከወይራ ዛፍ ጋር አነጻጸረ፣ ያዕቆ. ፭–፮።

ጌታ የክፍል ፻፩ ራዕይን የወይራ ዛፍ ቀጠል ብሎ ጠራ፣ ት. እና ቃ. ፻፩ ማስተዋወቂያ። ልዑል ሰው አገልጋዮቹን ወደ ወይን አትክልት ስፍራው እንዲሄዱ እና አስራ ሁለት የወይራ ዛፎች እንዲተክሉ ነገራቸው፣ ት. እና ቃ. ፻፩፥፵፫–፷፪።

የዋህ፣ የዋህነት

ንጹህ ወይም ኃጢያት የሌለው።

ከውድቀት በፊት አዳምና ሔዋን በየዋህነት ነበሩ፣ ፪ ኔፊ ፪፥፳፫። የንፁሃን ደም በእነርሱ ላይ ለምስክርነት ይቆማል፣ አልማ ፲፬፥፲፩።

እያንዳንዱ የሰው መንፈስ በመጀመሪያ የዋህ ነበር፣ ት. እና ቃ. ፺፫፥፴፰። ንጹሕ ትክክለኛ ካልሆኑት ጋር አይኮነኑም፣ ት. እና ቃ. ፻፬፥፯። ጆሴፍ እና ሀይረም ስሚዝ ከምንም ወንጀል የዋህ ነበሩ፣ ት. እና ቃ. ፻፴፭፥፮–፯።

ልጆች ከአለም መሰረት ጊዜ ጀምሮ ከኀጥያት ንጹህ ናቸው፣ ሙሴ ፮፥፶፬።

የዔድን ገነት። ዔድን *ተመልከቱ*

የዘለዓለም ህይወት። *ደግሞም* ህይወት፤ አክሊል፤ ከፍተኛነት፤ የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ፤ የሰለስቲያል ክብር *ተመልከቱ*

በእግዚአብሔር ፊት እንደ ቤተሰብ ለዘለአለም መኖር (ት. እና ቃ. ፻፴፪፥፲፱–፳፣ ፳፬፣ ፶፭)። ዘለአለማዊ ህይወት እግዚአብሔር ለሰው ከሰጠው ስጦታዎች ታላቁ ነው።

አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ፣ ዮሐ. ፮፥፷፰። እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት፣ ዮሐ. ፲፯፥፫ (ት. እና ቃ. ፻፴፪፥፳፬)። መልካሙን የእምነት ገድል ተጋደል፣ የዘላለምን ሕይወት ያዝ፣ ፩ ጢሞ. ፮፥፲፪።

ነፃነትን ወይም ዘለዓለማዊ ህይወትን ለመምረጥ ነፃ ናቸው፣ ፪ ኔፊ ፪፥፳፯ (ሔለ. ፲፬፥፴፩)። ስለመንፈሳዊ ነገር ማሰብ ዘለዓለማዊ ህይወት ነው፣ ፪ ኔፊ ፱፥፴፱። ወደ ዘለአለም በሚመራው ጠባቡ ጎዳና ላይ ናችሁ፣ ፪ ኔፊ ፴፩፥፲፯–፳። በክርስቶስ ማመን እና እስከመጨረሻ መፅናት ዘለዓለማዊ ህይወት ነው፣ ፪ ኔፊ ፴፫፥፬ (፫ ኔፊ ፲፭፥፱)።

ዘለዓለማዊ ሕይወት ያለው ሰው ሃብታም ነው፣ ት. እና ቃ. ፮፥፯ (ት. እና ቃ. ፲፩፥፯)። ከእግዚአብሔር ስጦታዎች ሁሉ ታላቅ ስጦታ የሆነውን ዘላለማዊ ህይወት ይኖርሃል፣ ት. እና ቃ. ፲፬፥፯ (ሮሜ ፮፥፳፫)። ጻድቅ በዚህ አለም ሰላም እና በወዲያኛው አለምም ዘለአለማዊ ህይወትን ይቀበላል፣ ት. እና ቃ. ፶፱፥፳፫። እስከ መጨረሻውም የሚቀጥል የዘለአለም ህይወት አክሊል ይኖረዋል፣ ት. እና ቃ. ፷፮፥፲፪ (ት. እና ቃ. ፸፭፥፭)። ለመቀየት ቢፈቀድላቸው ይቀበሉት የነበሩት፣ ይህን ወንጌል ካለማወቅ የሞቱት ሁሉ የእግዚአብሔር ሰለስቲያል መንግስት ወራሾች ይሆናሉ፣ ት. እና ቃ. ፻፴፯፥፯–፱።

የእግዚአብሔር ስራና ክብር የሰውን አለሟችነት እና ዘለአለማዊ ህይወትን ማምጣት ነው፣ ሙሴ ፩፥፴፱። ለታዛዡ ሁሉ እግዚአብሔር ዘለአለማዊ ህይወትን ይሰጣል፣ ሙሴ ፭፥፲፩።

የዘመን ቅድመ ተከተል

በተጨማሪም የዘመን ቅድመ ተከተልን ተመልከቱ።

የያሬድ ወንድም። *ደግሞም* ያሬዳውያን፤ ያሬድ *ተመልከቱ*

የመፅሐፈ ሞርሞን ነቢይ እርሱ እና ወንድሙ የህዝብ ቡድንን ከባቢሎን ማማ በምዕራብ ክፍለ አለም ወደሚገኘው የቃል ኪዳን ምድር መርተው በማውጣት የያሬዳውያን ሀገርን መሰረቱ (ኤተር ፩–፮)። ታላቅ እምነት ያለው ሰው ሆኖ ከጌታ ጋር ፊት ለፊት ተነጋገረ (ት. እና ቃ. ፲፯፥፩)። ታሪኩ በመፅሐፈ ኤተር የተመዘገበ ነው።

የያሬድ ወንድም ትልቅ እናም ኃያል ሰው በመሆኑ፣ እናም በጌታም በይበልጥ የሚወደድ ነበር፣ **ኤተር** ፩፥፴፬። በእምነቱ ምክንያት፣ የያሬድ ወንድም የጌታን ጣት አየ፣ **ኤተር** ፫፥፮–፱ (ኤተር ፲፪፥፳)። ክርስቶስ የመንፈስ ሰውነቱን ለያሬድ ወንድም አሳየ፣ **ኤተር** ፫፥፲፫–፳። ለያሬድ ወንድም ከተገለፀው በላይ የተገለፁ ታላቅ የሆኑ ነገሮች በጭራሽ አልነበሩም፣ **ኤተር** ፬፥፬። የያሬድ ወንድም ህዝቡን ስለንጉሳዊ አገዛዝ አስጠነቀቃቸው፣ **ኤተር** ፮፥፳፪–፳፫። ጌታ ለያሬድ ወንድም ሁሉንም ነገሮች አሳየው፣ **ኤተር** ፲፪፥፳፩። የያሬድ ወንድም በይበልጥ መፃፍ የሚችል ነበር፣ **ኤተር** ፲፪፥፳፬። በእምነት የያሬድ ወንድም የዜሪንን ተራራ አንቀሳቀሰ፣ **ኤተር** ፲፪፥፴።

የይሁዳ በትር። ይሁዳ፣ የያዕቆብ ልጅ—የይሁዳ በትር *ተመልከቱ*

የዮሐንስ ራዕይ። *ደግሞም* አቡቃለምሲስ፤ ዮሐንስ፣ የዘብዴዎስ ልጅ *ተመልከቱ*

ለሐዋሪያ ዮሐንስ የተሰጠውን ራዕይ የያዘ የአዲስ

ኪዳን የመጨረሻ መፅሐፍ። የአለም ታሪክን፣ በተ ለይም የመጨረሻ ቀናትን፣ እንዲያይ ተፈቀደለት (ራዕ. ፩፡፩–፪፣ ፩ ኔፊ ፲፬፡፲፰–፳፯፣ ት. እና ቃ. ፳፯)። የዮሐንስ ራዕይ ደግሞም አቡቃለምሲስ

ዮሐንስ ይህን ራዕይ የተቀበለው በጌታ ቀን፣ በእ ስያ ባህር ዳር፣ ከኤፌሶን ባልራቀው፣ ፍጥሞ በም ትባል ደሴት ላይ ነበር (ራዕ. ፩፡፱–፲)። የራዕዩ ትክ ክለኛ ቀን አይታወቅም።

ይህም መፅሐፍ የሚገባበት ቁልፎች በ፩ ኔፊ ፲፡፡–፲፰ እና በትምህርት እና ቃልኪዳኖች ፳፯ (ኤተር ፬፡፲፩–፲፯) ውስጥ ይገኛሉ።

ምዕራፍ ፩–፫ የመፅሐፉ ማስተዋወቂያ እና በእ ስያ ውስጥ ለሚገኙት ቤተክርስቲያናት ደብዳቤ ዎች ነበሩ። ዮሐንስ ደብዳቤውን የጻፈው ቅዱሳን ለአንዳንድ ችግሮችን መፍትሄ እንዲያገኙ ለመር ዳት ነበር። ምዕራፍ ፬–፭ የእግዚአብሔርን እና የክ ርስቶስን ክብር እና ጻድቅ ሀይል የሚያሳዩ ራዕዮ ችን ዮሐንስ የተቀበለበትን ይመዘግባሉ። በምዕ ራፍ ፮–፱፣ ፲፩ ውስጥ፣ ዮሐንስ በሰባት መሀተ ማት የታተመ መፅሀፍን እንዳየ፣ እያንዳንዱም መሀተም የምድርን አንድ ሺህ ጊዜአዊ ታሪክን እንደሚወክል መዘገበ። እነዚህ ምዕራፎች በመ ጀመሪያ በሰባተኛው መሀተም ስለሚሆኑት ድር ጊቶች ላይ ያተኩሩ ነበር (ራዕ. ፰–፱፣ ፲፩፡፩–፲፭ ተመልከቱ)። ምዕራፍ ፲ ዮሐንስ የበላውን መፅሀፍ ይገልጻሉ። ይህ መፅሀፍ ወደፊት የሚያከናውናቸው ተልዕኮን ይወክላል። ምዕራፍ ፲፪ ሰይጣን ሲያ ምጽ እና በተወረወረበት ጊዜ በሰማይ ስለተጀመ ረው ክፋት ራዕይ ይመዘግባል። በእዚያም የተጀ መረው ጦርነት በምድር ላይ ቀጥሏል። በምዕራፎች ፲፫፣ ፲፮–፲፱ ውስጥ፣ ዮሐንስ ሰይጣን የሚቆጣጠ ረውን ኃጢያተኛ የምድር መንግስትን ገልጿል፣ እጣ ፈንታቸውን፣ በተጨማሪም የክፉን በመጨ ረሻ መደምሰስንም መዝግቧል። ምዕራፍ ፲፱–፲፮ ከክርስቶስ ዳግም ምፅዓት በፊት በኃጢያት መካ ከል የቅዱሳንን ጽድቅን ይገልጻሉ። ምዕራፍ ፳–፳፪ አንድ ሺህ አመትን፣ ውብታማዋን አዲሲቱን ኢየ ሩሳሌም፣ እና የምድርን ታሪክ የመጨረሻ ድርጊ ቶችን ይገልጻሉ።

የዮሴፍ በትር። ኤፍሬም—የዮሴፍ ወይም የኤፍሬም በትር *ተመልከቱ*

የዮርዳኖስ ወንዝ

የዮርዳኖስ ወንዝ ከገሊላ ባህር ወደ ሙት ባህር ይፈሳል። ወንዙ ፤ ማይል (፤፳ኪሎ ሜትር) የረ ዘመ ነው እናም ከአርሞንዔም ተራራ ከሚመነጩ መንጮች የተሰራ ነው። ይህም በእስራኤል ውስጥ በጣም አስፈላጊ የሆነ ወንዝ ነው።

ከዚህ ወንዝ ጋር የተገናኙ ሁለት አስፈላጊ ድር ጊቶች እስራኤል እንድትሻገር ጌታ ወንዙን በሁለት መከፈሉ (ኢያ. ፫፡፲–፲፯) እና የኢየሱስ ክርስቶስ መጠመቅ ነበሩ (ማቴ. ፫፡፲፫–፲፯፣ ፩ ኔፊ ፲፡፱)።

የደህንነት አላማ። የቤዛነት ዕቅድ *ተመልከቱ*

የደማስቆ ሐናንያ። *ደግሞም ጳውሎስ ተመልከቱ*

በደማስቆ ጳውሎስን ያጠመቀው የክርስትያን ደቀ መዛሙርት (የሐዋ. ፱፡፲–፲፯፣ ፳፪፡፲፪)።

የደረት ኪስ። *ደግሞም ኡሪም እና ቱሚም ተመልከቱ*

ቅዱስ መጻህፍቶች ሁለት አይነት የደረት ኪሶ ችን ጠቅሰዋል፥ (፩) የወታደር መከላከያ ልብስ ወይም ጥሩር የፊት ለፊት ክፍል። በምሳሌአዊ ሁኔታ፣ ቅዱሳን የጽድቅንም ጥሩር እራሳቸውን ከክፉ ለመጠበቅ መልበስ ይገባቸዋል (ኢሳይ ያስ ፶፱፡፲፯፣ ኤፌ. ፮፡፲፬)። (፪) በሙሴ ህግጋት ውስጥ ሊቀ ካህናት ይለብሱት የነበረ ልብስ (ዘፀአ. ፳፰፡፲–፴፣ ፴፱፡፰–፳፩)። በሊኖ የተሰራና በእ ንቁ ድንጋዮች የተጌጠ ነበር። አንዳንዴም ከኡሪም እና ቱሚም ጋር ተገናኝቶ ይጠቀሳል (ት. እና ቃ. ፲፯፡፩፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፴፭፣ ፴፱፡፣ ፶፪)።

የጃክሰን አውራጃ፣ ምዙሪ (ዮኤስኤ)። *ደግሞም አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ተመልከቱ*

በመጨረሻው ቀናት የቅዱሳን መሰብሰቢያ ቦታ፣ ይህም ማለት፣ አዲሱን ኢየሩሳሌም የሚመሰርቱ በት ዋና ቦታ (ት. እና ቃ. ፶፯–፶፰፣ ፹፪፡፣ ፲፩፡፡–፲፪፣ ፲፭፡፡–፲፰)።

የጆሴፍ ስሚዝ ትርጉም (ጆ.ስ.ት.)። *ደግሞም ስሚዝ፣ ጆሴፍ ዳግማዊ ተመልከቱ*

ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በ፲፰፻፳፭ (እ.አ.አ.) የጀመ ረው የንጉስ ጄምስ ትርጉም መፅሐፍ ቅዱስ ግም ገማ ወይም ትርጉም። በእግዚአብሔር እንዲተረ ጉም እና ይህን እንደ ነቢይ ጥሪው ክፍል እንዲመ ለከተው ታዝዞ ነበር።

ምንም እንኳን ጆሴፍ አብዛኛውን ትርጉም በሐምሌ ፲፰፻፳፭ (እ.አ.አ.) ቢፈጽማቸውም፣ በ፲፰፻፳፯ (እ.አ.አ.) ውስጥ እስከሞተበት ጊዜ ድረስ ጽሁፎችን ለማሳተም እያዘጋጀ ለውጦችን እያስተካ ከለ ነበር። ምንም እንኳን በህይወቱ ጊዜ የትርጉሙ ክፍሎችን ቢያትምም፣ ስራውን በሙሉ ለማተም በህይወት ቢኖር ኖሮ ተጨማሪ ቅያሬዎችን ማድ ርግ ይችል ይሆን ነበር። እንደገና የተደራጀው የኋለ ኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን የጆሴፍ ስሚዝ የተነሳሳ ትርጉም የመጀመሪያ ቅጂን በ፲፰፻፳፰ (እ.አ.አ.) አሳተሙ። ከእዚያም ጊዜ በኋላ ብዙ ቅጂዎች አሳትመዋል።

ነቢዩ በትርጉሙ ጊዜ ብዙ ነገሮችን ተምሯል።

ብዙዎቹ የትምህርት እና ቃል ኪዳኖች ክፍሎችን (ለምሳሌ ት. እና ቃ. ፸፮፤ ፸፯፤ ፺፩፤ ፻፴፪) የተቀበለው በትርጉም ስራው ምክንያት ነው። ደግሞ፣ ጌታ በትምህርት እና ቃል ኪዳኖች ውስጥ የተመዘገቡትን ልዩ መመሪያዎች ለጆሴፍ ሰጠ (ት. እና ቃ. ፴፯፥፩፤ ፵፭፥፷–፷፩፤ ፸፮፥፲፭–፲፰፤ ፺፫፥፶፫፤ ፺፬፥፲፤ ፻፬፥፶፰፤ ፻፳፬፥፹፱)። አሁን በታላቅ ዋጋ ዕንቁ ውስጥ የሚገኙት መፅሐፈ ሙሴ እና የጆሴፍ ስሚዝ ማቴዎስ ከጆሴፍ ስሚዝ ትርጉም የተወሰዱ ናቸው።

የጆሴፍ ስሚዝ ትርጉም ከመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጠፍተው የነበሩትን ግልፅ እና ውድ ነገሮችን ዳግሞ መልሷል (፩ ኔፊ ፲፫)። ምንም እንኳን ይህ የቤተክርስያኗ ህጋዊ መፅሐፍ ቅዱስ ባይሆንም፣ ይህ ትርጉም ብዙ አስደናቂ አስተያየቶችን ያቀርባል እናም መፅሐፍ ቅዱስን በማስተዋል ታላቅ ዋጋ ያለው ነው። ይህም ደግሞ ስለ ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ መለኮታዊ ጥሪና አገልግሎት ምስክር ነው።

የጊዜዎች ምልክቶች። *ደግሞም ምልክት፤ የመጨረሻ ቀናት፣ የኋለኛው ቀናት፤ የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት ተመልከቱ*

እግዚአብሔር ለህዝቦቹ በስራው አስፈላጊ ነገር እንደደረሰ ወይም በቅርብ እንደሚደርስ ለማሳየት የሚሰጠው ድርጊቶች ወይም አጋጣሚዎች። በኋለኛው ቀናት፣ ለአዳኝ ዳግም ምፅዓት ብዙ ምልክቶች ተተንብየዋል። እነዚህ ምልክቶች ታማኝ ሰዎች የእግዚአብሔርን አላማ እንዲያውቁ፣ እንዲጠነቀቁ፣ እና እንዲዘጋጁ ይፈቅድላቸዋል።

የእግዚአብሔር ቤት ተራራ በተራሮች ራስ ላይ ጸንቶ ይቆማል፣ ኢሳ. ፪፥፪–፫። ጌታ ምልክትን ያቆማልእናም እስራኤልን ይሰበስባል፣ ኢሳ. ፭፥፳፮ (፪ ኔፊ ፲፭፥፳፮–፴)። ፀሐይም በወጣች ጊዜ ትጨልማለች፥ ጨረቃም በብርሃኑ አያበራም፣ ኢሳ. ፲፫፥፲ (ኢዩ. ፫፥፲፭፤ ት. እና ቃ. ፳፱፥፲፬)። ሰዎች ሕጉን ተላልፈዋል፣ የዘላለሙንም ቃል ኪዳን አፍርሰዋል፣ ኢሳ. ፳፬፥፭። የኔፋውያን ቃል ከአፈር ወጥቶ ይጮኻል፣ ኢሳ. ፳፱፥፬ (፪ ኔፊ ፳፯)። እስራኤል በሀይል ትሰበሰባለች፣ ኢሳ. ፵፱፥፳፪–፳፫ (፩ ኔፊ ፳፩፥፳፪–፳፫፤ ፫ ኔፊ ፳–፳፩)። እግዚአብሔር የማይፈርስ መንግሥት ያስነሣል፣ ዳን. ፪፥፵፬ (ት. እና ቃ. ፷፭፥፪)። ጦርነት፣ ህልሞች፣ እና ራዕዮች ከዳግም መፅዓት በፊት ይታያሉ፣ ኢዩ. ፪። አሕዛብንም ሁሉ በኢየሩሳሌም ላይ ለሰልፍ ይሰበሰባሉ፣ ዘካ. ፲፬፥፪ (ሕዝ. ፴፰–፴፱)። እንደ ምድጃ እሳት የሚነድድ ቀን ይመጣል፣ ሚል. ፬፥፩ (፫ ኔፊ ፳፭፥፩፤ ት. እና ቃ. ፻፴፫፥፷፬፤ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፴፯)።

ከዳግም ምፅዓት በፊት ታላቅ አደጋዎች ይመጣሉ፣ ማቴ. ፳፬ (ጆ.ስ.—ማቴ. ፩)። ጳውሎስ ክህደትን እና የመጨረሻ ቀናት አስቃቂ ጊዜዎችን ገለጸ፣ ፪ ጢሞ. ፫–፬። ሁለት ነቢያት ይገደላሉ እናም በኢየሩሳሌም ከሞት ይነሳሉ፣ ራዕ. ፲፩ (ት. እና ቃ. ፸፯፥፲፭)። ወንጌል በመጨረሻው ቀናት በመላእክት አገልግሎት በዳግም ይመለሳሉ፣ ራዕ. ፲፬፥፮–፯ (ት. እና ቃ. ፲፫፤ ፳፯፤ ፻፲፥፲፩–፲፮፤ ፻፳፰፥፳–፳፬)። ባቢሎስ ትመሰረታለች እናም ትወድቃለች፣ ራዕ. ፲፯–፲፰።

እስራኤል በሀይል ትሰበሰባለች፣ ፩ ኔፊ ፳፩፥፲፫–፳፮ (ኢሳ. ፵፱፥፲፫–፳፮፤ ፫ ኔፊ ፳–፳፩)። እናም እውነት እላችኋለሁ፣ እነዚህ ነገሮች፣ ህዝቤን የእስራኤልን ቤት፣ ለረጅም ጊዜ ከተበተኑበት የምሰበስበት፣ እናም በድጋሚም ፅዮንንም በመካከላቸው የምመሰርትበት የሚፈፀሙበትን ጊዜ ታውቁ ዘንድ ምልክትን እሰጣችኋለሁ፣ ፫ ኔፊ ፳፩፥፩። ጊዜውን ታውቁ ዘንድ ይህ ምልክት ነው፣ ሞር. ፳።

ላማናውያንም ያብባሉ፣ ት. እና ቃ. ፵፱፥፳፬–፳፭። ኃጢያተኞች ኃጢያተኞችን ይገድላሉ፣ ት. እና ቃ. ፷፫፥፴፪–፴፫ (ራዕ. ፱)። በሁሉም ህዝቦች ላይ ጦርነት ይፈሳል፣ ት. እና ቃ. ፹፯፥፪። ምልክቶች የንጥረ ነገር ብጥበጣ፣ እና መላእክቶች ለጌታ መምጣት መንገድን ያዘጋጃሉ፣ ት. እና ቃ. ፹፰፥፹፯–፺፩። ጭለማ ምድርን ይሸፍናል፣ ት. እና ቃ. ፻፲፪፥፳፫–፳፬። ጌታ ቅዱሳንን ለዳግም ምፅዓት እንዲዘጋጁ አዘዘ፣ ት. እና ቃ. ፻፴፫።

የጋራ ስምምነት። *ደግሞም የቤተክርስቲያን መሪዎችን መደገፍ፤ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ተመልከቱ*

የቤተክርስቲያን አባላት በቤተክርስቲያኗ እንዲያገለግሉ የተጠሩትን፣ እንዲሁም ድጋፋቸው የሚያስፈልገው ለሎች የቤተክርስቲያን ውሳኔዎችን የሚደግፉባቸው መሰረታዊ መመሪያ ነው፣ በብዙም ጊዜ ይህ የሚታየው የቀኝ እጅን በማንሳት ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተክርስቲያኑ መሪነት ይቆማል። በመንፈስ ቅዱስ መነሳሳት በኩልም የቤተክርስቲያን መሪዎቹን በአስፈላጊ ስራዎች እና ውሳኔዎች ላይ መመሪያ ይሰጣቸዋል። ነገር ግን፣ የቤተክርስቲያኗ አባላት ሁሉ የመሪዎችን ስራዎችና ውሳኔዎች የመደገፍ ወይም ያለመደገፍ መብትና እድል አላቸው።

ሕዝቡም ሁሉ በአንድ ድምፅ. . . መለሱ፣ ዘፀአ. ፳፬፥፫ (ዘኁል. ፳፯፥፲፰–፲፱)።

ሐዋርያትና ሽማግሌዎች በአንድ ልብ ተሰበሰቡ፣ የሐዋ. ፲፭፥፳፭።

ማንም ሰው ያለቤተክርስቲያኗ ድምጽ ሹመት አይሰጠው፣ ት. እና ቃ. ፳፥፷፭–፷፮። ሁሉም ነገሮች በጋራ ስምምነት ይደረጉ፣ ት. እና ቃ. ፳፮፥፪

(ት. እና ቃ. ፳፯፡፲፫)። ሁሉም ነገሮች በጋራ ስም ምነት ይደረጉ፣ ት. እና ቃ. ፲፬፡፳፩።

የጋድያንቶን ዘራፊዎች። *ደግሞም የሚስጥር ስብሰባ ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ በክፉው ኔፋውያን ጋድያንቶች የተመሰረቱ የዘራፊዎች ቡድን። ድር ጅታቸው በሚስጥርና በሰይጣናዊ መሀላ ላይ የተ መሰረተ ነው።

ጋድያንቶን የኔፋውያን ህዝብ ጥፋት ምክንያት ነው፣ ሔሌ. ፪፡፲፪–፲፫። ዲያብሎስ ለጋድያንተን የሚስጥር መሀላዎችና ቃል ኪዳኖች ሰጠ፣ ሔሌ. ፮፡፲፯–፴፪። ሚስጥራዊ ህብረት የያሬዳውያን ህዝ ቦችን ጥፋት ምክንያት ነው፣ ኤተር ፰፡፲፭–፳፭።

የጌታ ቀን። የሰንበት ቀን፤ የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት፤ ፍርድ፣ የመጨረሻው *ተመልከቱ*

የጌታ ቤት። ቤተመቅደስ፣ የጌታ ቤት *ተመልከቱ*

የጌታ እራት። ቅዱስ ቁርባን *ተመልከቱ*

የጌታ የወይን አትክልት ስፍራ። *ደግሞም* እስራኤል፣ እርሻ *ተመልከቱ*

ለመንፈሳዊ አገልግሎት እርሻ የሚሰጥ ምሳሌ። በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ፣ የጌታ የወይን አት ክልት ስፍራ በብዙ ጊዜ የእስራኤል ቤትን ወይም በምድር ላይ ያለውን የእግዚአብሔር መንግስት የሚጠቁም ነው። ይህ አንዳንዴም በአጠቃላይ ስለ አለም ህዝቦች የሚጠቁም ነው።

የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር ወይን ቦታ እርሱ የእስራኤል ቤት ነው፣ ኢሳ. ፭፡፯ (፪ ኔፊ ፲፭፡፯)።

ኢየሱስ ስለወይን አትክልት ስፍራ አገልጋዮች ምሳሌ ሰጠ፣ ማቴ. ፳፡፩–፲፮።

እስራኤልን በጌታ ወይን ስፍራውስጥ ከለማው የወይራ ዛፍ ጋር አመሳሰለ፣ ያዕቆ. ፭። የጌታ አገ ልጋዮች የወይን ስፍራውን ለመጨረሻ ጊዜ ይከ ረክማሉ፣ ያዕቆ. ፮።

በወይኑ እርሻዬ የሚሰሩቱን በታላቅ በረከት እባ ርካቸዋለሁ፣ ት. እና ቃ. ፳፩፡፱ (አልማ ፳፯፡፲፱)። በወይን አትክልት ስፍራዬ ለመጨረሻ ጊዜ ስሩ፣ ት. እና ቃ. ፶፫፡፳፯።

የጌታ የወይን አትክልት ቦታ። የጌታ የወይን አትክልት ስፍራ *ተመልከቱ*

የጌታ ጸሎት። *ደግሞም* ጸሎት *ተመልከቱ*

ለሁሉም ጸሎቶች እንደንድፍ የሚያገለግል አዳኝ ለደቀመዛሙርቶቹ ያቀረበው ጸሎት (ማቴ. ፮፡፱–፲፫፣ ፫ ኔፊ ፲፫፡፱–፲፫)።

የጠርሴስ ሳዖል። ጳውሎስ *ተመልከቱ*

የጠፉት ጎሳዎች። እስራኤል—የጠፉት የእስራኤል አስር ጎሳዎች *ተመልከቱ*

የጥበብ ቃል

ለቅዱሳን ስጋዊ እና መንፈሳዊ ጥቅም ጌታ የገለ ጸው የጤንነት ህግ (ት. እና ቃ. ፹፱)። አሁን ይህም የጥበብ ቃል ተብሎ ይታወቃል። ጌታ ሁልጊዜም ተከታዮቹን የጤና መስረታዊ መርሆችን ያስተም ራል። ጌታ ለጆሴፍ ስሚዝ የትኛውን ምግብ መመ ገብ እንደሚገባ እና የትኛውን ምግብ ማስወገድ እንደሚገባ፣ እንዲሁም የጥበብ ቃልን ለሚያከ ብሩ ምድራዊ እና መንፈሳዊ በረከቶች ቃል ኪዳን በመግባት ገለጸ።

የወይን ጠጅና የሚያሰክርን ነገር ሁሉ አትጠጡ፣ ዘሌዋ. ፲፡፱። የወይን ጠጅ ፈዘኛ ያደርጋል፥ ብርቱ መጠጥም ጠበኛ ያደርጋል፣ ምሳ. ፳፡፩። የሚያሰ ክርም መጠጥ ለሚጠጡት መራራ ይሆናል፣ ኢሳ. ፳፬፡፱። ዳንኤልም በንጉሡ መብልና በሚጠጣው ጠጅ እራሱን አላረከሰም፣ ዳን. ፩፡፰።

ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል፣ ፩ ቆሮ. ፫፡፲፯–፲፯። ሰካሮች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወር ሱም፣ ፩ ቆሮ. ፮፡፲ (ገላ. ፭፡፳፩)።

ከስጋ እንዲቆጠብ የሚከለክልም በእግዚአብሔር የተሾመ አይደለም፣ ት. እና ቃ. ፵፱፡፲፰–፳፩። ከምድር የሚመጡት ነገሮች ሁሉ በብልጫ ሳይ ሆን በጥበብ ይጠቀሙባቸው፣ ት. እና ቃ. ፶፱፡፳። ጌታ የወይን ጠጅ፣ የሚያሰክር መጠጥ፣ ትምባሆ፣ እና ትኩስ መጠጦችን እንዳይጠቀሙባቸው ቅዱ ሳንን መከረ፣ ት. እና ቃ. ፹፱፡፩–፱። ለምለሞች፣ ፍሬዎች፣ ስጋ፣ እና እህል ለሰው እና ለእንስሳት ጥቅም ተመድበዋል፣ ት. እና ቃ. ፹፱፡፣–፲፯። ለጥ በብ ቃል ታዛዥ መሆን ምድራዊ እና መንፈሳዊ በረከቶችን ያመጣል፣ ት. እና ቃ. ፹፱፡፲፰–፳፩።

የጥፋት ልጆች። *ደግሞም* መንፈሳዊ ሞት፤ ሲያል፣ ኩነኔ፤ ይቅርታ የሌለው ኃጢያት፤ ዲያብሎስ *ተመልከቱ*

ከእርሱ ጋር ለዘለአለም የሚሰቃዩ የሰይጣን ተከ ታዮች። የጥፋት ልጆች በተጨማሪም (፩) ሰይጣንን የተከተሉት እና ከምድረ ህይወት በፊት ከሰማይ በአ መፅ ምክንያት ተጥለው የወጡት (፪) ወደ ዚህ አለም በስጋ ሰውነት እንዲወለዱ የተፈቀደላቸው ነገር ግን ከእዚያም በኋላ ሰይጣንን ያገለገሉ እና በእግዚአ ብሔር ላይ ያመጹት ናቸው። በእዚህ በሁለተኛው ቡድን ውስጥ ያሉት ከሞት ይነሳሉ ነገር ግን ከሁለ ተኛው (መንፈሳዊ) ሞት አይቤዙም እናም በክብር መንግስት ውስጥ ለመኖር አይችሉም (ት. እና ቃ. ፹፰፡፴፪፣ ፴፪)።

የጳውሎስ መልእክቶች

ከጥፋት ልጅ በቀር ከእነርሱ ማንም አልጠፋም፣ ዮሐ. ፲፯፡፲፪። እንደገና ለንስሐ እነርሱን ማደስ የማይቻል ነው፣ ዕብ. ፮፡፬–፮ (ዕብ. ፲፡፳፮–፳፱)።

ምህረት ለዚያ ሰው ምንም ሥፍራ አይኖራትም፤ ስለዚህ የመጨረሻ ዕጣው ማለቂያ የሌለውን ቅጣት መጋፈጥ ነው፣ ሞዛያ ፪፡፴፯–፴፱። እርሱ ቤዛነት እንዳልተደረገለት ይሆናል፣ ሞዛያ ፲፮፡፭። ጥቅ ምን ለማግኘት፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ድንቅ ነገር የሚክድ እንደጥፋት ልጅ ይሆናል፣ ፫ ኔፊ ፳፱፡፮። በዚህም ምድር ይሁን ወይም በሚመጣው ይህረ ትን አያገኙም፣ ት. እና ቃ. ፫፯፡፴–፴፪ (ት. እና ቃ. ፴፬፡፴፭፣ ፴፭፡፲፣ ፲፴፪፡፳፯)። ከሁለተኛ ው ሞት የማይ ድኑት እነርሱ ብቻ ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፫፯፡፴–፴፰። የጥፋት ልጆች ከተቀበሉት በኋላ መንፈስ ቅዱስን ይክዳሉ፣ ት. እና ቃ. ፫፯፡፴፭። የጥ ፋት ልጆች ወልድን አብ ከገለጸው በኋላ ይክዳሉ፣ ት. እና ቃ. ፫፯፡፴፮።

ቃየን ጥፋት ተብሎ ይጠራል፣ ሙሴ ፭፡፳፭–፳፯።

የጳውሎስ መልእክቶች። *ደግሞም ጳውሎስ፤ የእያንዳንዱ መልእክቶች ርዕሶች ተመልከቱ*

ጳውሎስ ለቤተክርስቲያኗ አባላት በመጀመሪያ የጻፋቸው ደብዳቤዎች የነበሩ የአዲስ ኪዳን አስራ አራት መፅሐፎች። እነዚህ በቡድኖች እንዲህ ለመ ከፋፈል ይችላሉ፥

፩ እና ፪ ተሰሎንቄ (፴–፴፩ ዓ.ም.)

ጳውሎስ መልእክቶችን ለተሰሎንቄ የጻፈው በሁ ለተኛው የሚስዮን ጉዞ ከቆሮንቶስ ነበር። በተሰሎ ንቄ የሰራው በሐዋርያት ስራ ፲፯ ውስጥ ተገልጿል። ወደ ተሰሎንቄ ለመመለስ ፈለገ፣ ነገር ግን አልቻ ለም (፩ ተሰ. ፪፡፲፯)። ስለዚህ ተቀያሪዎችን እንዲ ያስደስት እና እንዴት እንደሆኑ ዜና እንዲያመጣ ለት ጢሞቴዎስን ላከው። የመጀመሪያው መልእክት የጢሞቴዎስ በደህንነት መመለስ ምስጋና ውጤት ነው። ሁለተኛው መልእክት የተጻፈው ከእዚያ ጊዜ ከአጭር ጊዜ በኋላ ነበር።

፩ እና ፪ ቆሮንቶስ፣ ገላትያ፣ ሮሜ (በ፴፭–፴፯ ዓ.ም.)

ጳውሎስ በሶስተኛው የሚስዮን ጉዞው ለቆሮን ቶስ ሰዎች መልእክቱን የጻፈው ጥያቄዎችን ለመ መለስ እና በቆሮንቶስ ቅዱሳን መካከል ያለውን ስህ ተት ለማስተካከል ነበር።

ወደ ገላትያ ሰዎች የጻፈው መልእክት በገላትያ ውስጥ ለነበሩት ብዙ ቤተክርስቲያናት ይሆን ነበር። አንዳንድ የቤተክርስቲያን አባላት የአይሁዳ ህግን ለማክበር ወንጌሉን ትተው ይሄዱ ነበር። በእዚህ ደብዳቤ፣ ጳውሎስ የሙሴ ህግ አላማን እና የመን ፈሳዊ ሀይማኖት ዋጋን ገለጸ።

ጳውሎስ ከቆሮንቶስ ወደ ሮሜ ሰዎች መልእ ክትን የጻፈው፣ እነርሱን ለመጎብኘት ተስፋ ለነበ ረው ጊዜ የሮሜ ቅዱሳንን ለማዘጋጀት ነበር። ደብ ዳቤው ደግሞም ወደ ክርስቲያንነት በተቀየሩ አን ዳንድ አይሁዶች ይከራከሩበት የነበረውን ትምህ ርት ያረጋግጣል።

ፊልጵስዮስ፣ ቆላስይስ፣ ኤፌሶን፣ ፊልሞን፣ ዕብራውያን (፴–፴፪ ዓ.ም.)

ጳውሎስ እነዚህን መልእክቶች የጻፈው ለመ ጀመሪያ ጊዜ በሮሜ እስር ቤት ውስጥ በነበረበት ጊዜ ነበር።

ጳውሎስ ለፊልጵስዮስ መልእክቱን የጻፈው ለፊ ልጵስዮስ ሰዎች ያለውን ምስጋና እና ፍቅር ለመግ ለፅ እና ለብዙ ጊዜ በመታሰሩ ከነበራቸው የተስፋ መቁረጥ እንርሱን ለማስደሰት ነበር።

ጳውሎስ ወደ ቆላስይስ ሰዎች መልእክትን የላ ከው የቆላስይስ ቅዱሳን ወደ ከፍተኛ ስህተት እየሄዱ እንደሆኑ በደረሰው ዜና ምክንያት ነበር። ፍጹም ነት የሚመጣው የክርስቶስ አይነት ጸባይ በማግኘት ሳይሆን የውጪ ስነስርዓቶችን በማከናወን ብቻ ነው ብለው ያምኑ ነበር።

ወደ ኤፌሶን ሰዎች መልእክቱ ስለክርስቶስ ቤተክርስቲያን ትምህርቶችን ስለያዘ በጣም አስ ፈላጊ ነበር።

ወደ ፊልሞን ሰዎች የላከው መልእክት ጌታውን ስለዘረፈው እና ወደ ሮሜ ስለሸሸው ባሪያ አናሲሞስ በሚመለከት ለፊልሞን የላከው የግል ደብዳቤ ነበር። ጳውሎስ አናሲሞስ ይቅርታ እንዲሰጠው በመጠየቅ አናሲሞስን ወደ ጌታው መልሶ ላከው።

ጳውሎስ ወደ ዕብራውያን የጻፈው መልእክት የቤተክርስቲያኗ የአይሁዳ አባላትን የሙሴ ህግ በክ ርስቶስ እንደተሟላ እና የክርስቶስ ወንጌል ይህን ተክቶ እንደመለሰው ለማሳመን ነበር።

፩ እና ፪ ጢሞቴዎስ፣ ቲቶ (፴፬–፴፭ ዓ.ም.)

ጳውሎስ እነዚህን መልእክቶች የጻፈው በመጀመ ሪያ ከሮሜ እስር ቤት ከተለቀቀ በኋላ ነበር።

ጳውሎስ ወደ ኤፌሶን ተጓዘ፣ በእዚያም ጢሞቴ ዎስን የትምህርት ግምቶችን እንዲያቆም ትቶት በኋላም ለመመለስ እያሰበ ሄደ። የመጀመሪያውን መልእክቱን፣ ምናልባት ከመቄዶንያ፣ ጢሞቴዎ ስን ለመምከር እና ሀላፊነቱን በማሟላት ለማበረታ ታት የጻፈው ነበር።

ጳውሎስ መልእክትን ወደ ቲቶ የላከው ከእስር ቤት በወጣበት ጊዜ ነበር። ቲቶ የሚያገለግልበትን ቀርጤስ ገንብቶም ይሆን ነበር። ደብዳቤው ስለጳጵቅ ኑሮ እና ስለ ቤተክርስቲያኗ ውስጥ ስነስርዓት ነበር።

ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ሁለተኛውን ደብዳቤ የጻ ፈው፣ ከጳውሎስ ስማዕት አጭር ጊዜ በፊት፣ ለሁለ ተኛ ጊዜ በእስር ቤት ውስጥ እያለ ነበር። ይህ መል እክት የጳውሎስን የመጨረሻ ቃላት ይዟል እናም

ሞትን በምን አይነት ጉብዝና እና እምነት እንደተ ቋቋመ ያሳያል።

የፓትሪያርክ በረከቶች። *ደግሞም ሟች አባት፤ ወንጌል ሰባኪ፤ የአባቶች አለቃ፣ ፓትሪያርክ ተመልከቱ*

በተሾሙ ፓትሪያርኮች ለብቁ የቤተክርስቲያኗ አባላት የሚሰጡ በረከቶች። የፓትሪያርክ በረከቶች በረከቱን ለሚቀበለው ሰው የጌታን ምክር ይይዛሉ እናም ሰው በእስራኤል ቤት ውስጥ ያላቸውን ዝርያ ይገልጻሉ። አባቶች እንደቤተሰቦቻቸው አለቃ ልዩ በረከቶችን ለመስጠት ይችላሉ፣ ነገር ግን እንደዚህ አይነት በረከቶች አይመዘገቡም ወይም በቤተክርስቲያኗ አይጠበቁም።

እስራኤልም ቀኝ እጁን ዘርግቶ በኤፍሬም ራስ ላይ አኖረው፣ ዘፍጥ. ፵፰፡፲፬። ያዕቆብ ልጆቹን እና ዘሮቹን ባረከ፣ ዘፍጥ. ፵፱። ሌሂ ትውልዶቹን ባረከ፣ ፪ ኔፊ ፩፡፮–፲፩።

ያህዌህ። *ደግሞም ኢየሱስ ክርስቶስ፤ ያለና የሚኖር ተመልከቱ*

የእስራኤል አምላክ ቃል ኪዳን ወይም ትክክለኛ ስም። ይህም "ዘለአለማዊ ያለና የሚኖርን" ይጠቁማል (ዘፀአ. ፫፡፲፬፤ ዮሐ. ፰፡፶፰)። ያህዌህ የቅድመ ምድር ኢየሱስ ክርስቶስ ነው እናም ወደ ምድር እንደ ማርያም ልጅ መጣ (ሞዛያ ፲፡፰፤ ፲፭፡፭፤ ፲ ኔፊ ፲፭፡፩–፳)። ብዙም ጊዜ፣ ጌታ የሚለው ቃል በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሲታይ፣ ይህም "ያህዌህ" ማለት ነው።

ያህዌህ ክርስቶስ ነው፣ ያህዌህ በጥንት ነቢያት የታወቀ ነው (ዘፀአ. ፮፡፫፤ አብር. ፩፡፲፯)። ሐዋሪያው ጳውሎስ ክርስቶስ የብሉይ ኪዳን ያህዌህ እንደነበረ አስተማረ (ዘፀአ. ፲፯፡፮፤ ፩ ቆሮ. ፣ ፡፩–፱)። በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ የያሬድ ወንድም የቅድመ ምድር ክርስቶስን አየ እናም አመለከ (ኤተር ፫፡፲፫–፲፭)። ሞሮኒ ደግሞም ክርስቶስን "ያህዌህ" ብሎ ጠራ (ሞሮኒ ፣፡ ፴፱)። በከርትላንድ ቤተመቅደስ ውስጥ፣ ጆሴፍ ስሚዝ እና ኦሊቨር ካውደሪ ከሞት የተነሳውን ያህዌህ አዩ (ት. እና ቃ. ፺፣፡፫–፱)።

ያለማባት። *ጋብቻ፣ መጋባት ተመልከቱ*

ያለና የሚኖር። *ደግሞም ኢየሱስ ክርስቶስ፤ ያህዌህ ተመልከቱ*

የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አንዱ ስም።

እግዚአብሔርም ሙሴን፣ "ያለና የሚኖር" እኔ ነኝ አለው፣ ዘፀአ. ፫፡፲፬–፲፭። እኔ እግዚአብሔር ነኝ፣ ዘፀአ. ፮፡፪–፫።

አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ፣ ዮሐ. ፰፡፶፰–፶፱።

ታላቁ ያለና የሚኖር ያለውን የኢየሱስ ክርስቶስን ድምጽ አድምጡ፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፩ (ት. እና ቃ. ፴፯፡፩፣ ፴፱፡፩)።

ያልተቀደሰ። *እግዚአብሔርን የሚጠላ ተመልከቱ*

ያሬዳውያን። *ደግሞም መፅሐፈ ሞርሞን፤ የያሬድ ወንድም፤ ያሬድ ተመልከቱ*

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ የያሬድ፣ የወንድሙ፣ እና የጓደኞቻቸው ትውልዶች የሆኑ ህዝቦች (ኤተር ፩፡፴፫–፴፭)። በእግዚአብሔር ከባቢሎን ማማ ወደ ቃል ኪዳን ምድር ወደ አሜሪካዎች ተመርተው ነበር (ኤተር ፩፡፴፪–፴፫፣ ፪–፫፣ ፮፡፩–፲፯)። በአንድ ጊዜ ብዙ ሚልዮን ህዝቦች የነበራት ሀገር ቢኖራቸውም፣ በኃጢያት ምክንያት በመጣ ጦርነት ምክንያት ተደምስሰው ነበር (ኤተር ፲፡–፲፩)።

ያሬድ። *ደግሞም የያሬድ ወንድም፤ ያሬዳውያን ተመልከቱ*

ከወንድሙ ጋር የህዝብ ቡድንን ከባቢሎን ማማ በምዕራብ ክፍለ አለም ወደሚገኘው የቃል ኪዳን ምድር መርቶ ያወጣ የመፅሐፈ ሞርሞን መሪ (ኤተር ፩፡፴፫–፪፡፩)።

ያሬድ ወንድሙን የቤተሰቦቻቸውን እና የወንድሞቻቸውን ቋንቋ ጌታ እንዳያምታታ እንዲጸልይ ጠየቀ፣ ኤተር ፩፡፴፭–፴፯። ወደ ባሕር ተጓዙ እናም ለአራት ዓመታት በእዚያ ኖሩ፣ ኤተር ፪፡፲፫። ወደ ቃል ኪዳን ምድር በመርከብ ሄዱ፣ ኤተር ፮፡፭–፲፪።

ያንግ፣ ብሪገም

በዚህ ዘመን የመጀመሪያ ሐዋርያ እናም የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ሁለተኛ ፕሬዘደንት። ቅዱሳንን ወደ ምዕራብ ከናቩ፣ ኢሊኖይ ወደ ሶልት ሌክ ሸለቆ መራቸው እናም በምዕራብ ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ታላቅ ፈር ቀዳጅ ነበር።

ብሪገም ያንግ በአስራ ሁለቱ ሐዋሪያት ላይ ፕሬዘደንት እንዲሆን ተጠራ፣ ት. እና ቃ. ፲፳፱፡፲፳፯። ብሪገም ያንግ ለአገልግሎቱ ተሞግሷል እና ከወደፊት ወደውጪ ጉዞም ፋታ አገኘ፣ ት. እና ቃ. ፲፳፯። ጌታ ብሪገም ያንግን ቅዱሳን ወደ ምዕራብ ሲጓዙ እንዴት እንደሚያደራጅ መመሪያ ሰጠው፣ ት. እና ቃ. ፲፴፯። ብሪገም ያንግ በመንፈስ አለም ውስጥ ምርጥ ከነበሩት አንዱ ነበር፣ ት. እና ቃ. ፲፴፯፡፲፫።

ያዕቆብ፣ የሌሂ ልጅ። *ደግሞም ሌሂ፣ የኔፊ አባት ተመልከቱ*

የመፅሐፈ ሞርሞን ነቢይ እና በ፪ ኔፊ እና በያ

ዕቁብ መፅሀፎች ውስጥ የተለያዩ ስብከቶች ጸሀፊ (፪ ኔፊ ፮–፲፩፣ ያዕቆ. ፩–፯)።

መፅሐፈ ያዕቆብ፣ በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ ሶስ ተኛ መፅሐፍ። ምዕራፍ ፩ ኔፊ የተቀደሱ መዝገቦች ለያዕቆብ አሳልፎ እንደሰጠ እና ከእዚያም ያዕቆብ ንና ወንድሙን ዮሴፍን ለህዝቡ ካህናት እና መም ህሮች እንዲሆኑ ቀደሰ። ምዕራፍ ፪–፬ ህዝቡን በስ ነምግባር ንጹህ እንዲሆኑ የሚገስጹ ስብከቶች። ያዕ ቆብ ደግሞም ስለሚያድነው መሲህ መምጣት አስ ተማረ፣ እና በሚመጣበት ጊዜ በእስራኤል ውስጥ ለምን አንዳንዶች እንደማይቀበሉት ምክንያትን ሰጠ። ምዕራፍ ፭–፯ የያዕቆብን ምስክር እና ስለ እስራኤል ህዝብ ታሪክ እና ተልዕኮ ነቢያዊ ምሳሌ የያዙ ናቸው። ምዕራፍ ፯ በያዕቆብ መለኮታዊ ምስ ክር ስለተሸነፈው ሼረም ስለሚባለው የተማረ ተቃ ዋሚ ታሪክ ይዟል።

ያዕቆብ፣ የእልፍዮስ ልጅ

በምድራዊ አገልግሎቱ ጊዜ ኢየሱስ ከመረጣ ቸው አስራ ሁለት ሐዋሪያት መካከል አንዱ (ማቴ. ፲፡፫፣ ማር. ፫፡፲፰፣ ሉቃ. ፮፡፲፭፣ የሐዋ. ፩፡፲፣)።

ያዕቆብ፣ የዘብዴዎስ ልጅ

በምድራዊ አገልግሎቱ ጊዜ ኢየሱስ ከመረጣ ቸው አስራ ሁለት ሐዋሪያት መካከል አንዱ ከወ ንድሙ ዮሐንስ ጋር የተመረጠ ነበር። በአንዳንድ ልዩ ጊዜዎች ከኢየሱስ ጋር እንዲሆኑ ከተመረ ጡት ሶስት ሐዋሪያት አንዱ፥ በኢያኢሮስ ሴት ልጅ ከሞት መነሳት ጊዜ (ማር. ፭፡፴፯)፣ በመለወጥ ጊዜ (ማቴ. ፲፯፡፩፣ ማር. ፱፡፪፣ ሉቃ. ፱፡፳፰)፣ እና በጌ ቴሴማኒ (ማቴ. ፳፮፡፴፯፣ ማር. ፲፬፡፴፫)። ከጴጥ ሮስ እና ከዮሐንስ ጋር ጆሴፍ ስሚዝን እና ኦሊ ቨር ካውደሪን በመሾም፣ የመልከ ጼዴቅ ክህነትን ወደ ምድር በዳግም መለሰ (ት. እና ቃ. ፳፯፣ ፲፪፣ ፲፳፰፡፳፡፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡ ፫፪)።

ያዕቆብ፣ የይስሐቅ ልጅ። *ደግምም ዔሳው፤ እስራኤል፣ ይስሐቅ ተመልከቱ*

የብሉይ ኪዳን የአባቶች አለቃና ነቢይ፣ የይስ ሀቅ እና የርብቃ መንታ ወንድ ልጆች ታናሹ (ዘፍጥ. ፳፭፡፲፱–፳፯)። ያዕቆብ ከወንድሙ ዔሳው በላይ በኩርን አገኘ። ይህም ያዕቆብ ብቁ ሆኖ እና በቃል ኪዳን ውስጥ ሲያገባ፣ ዔሳው በኩሩን በመጥላቱ እና ከቃል ኪዳን ውጪ በማግባቱ ምክንያት ነው (ዘፍጥ. ፳፭፡፴–፴፪፣ ፳፯፡፴፣ ፴፪፡፴፭፣ ፳፯፡፣ ፳፰፡፭–፱፣ ዕብ. ፲፪፡፲፯)።

ርብቃ ከጌታ ዔሳው ያዕቆብን እንደሚያገለ ግል ተማረች፣ ዘፍጥ. ፳፭፡፳፫። ከዔሳው በኩር ነትን ገዛ፣ ዘፍጥ. ፳፭፡፳፱–፴፪። ወደ ሰማይ ስለ ሚደርስ መሰላል አለመ፣ ዘፍጥ. ፳፰። ያልን እና ራሔልን አገባ፣ ዘፍጥ. ፳፱፡፩–፴። አስራ ሁለት ወንድ ልጆች እና አንድ ሴት ልጅ ወለደ፣ ዘፍጥ. ፳፱፡፴፩–፴፡፳፪፣ ፴፭፡፲፯–፳። ባላን እና ዘለፋን አገባ፣ ዘፍጥ. ፴፡፫–፴፡ ፴። ሰሙ ወደ እስራኤል ተቀየረ፣ ዘፍጥ. ፴፪፡፳፰። እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየ፣ ዘፍጥ. ፴፪፡፴። ዮሴፍን ከልጆቹ ሁሉ ይልቅ ይወደው ነበር፣ ዘፍጥ. ፴፯፡፫። ከቤተሰቡ ጋር ወደ ግብፅ ሄደ፣ ዘፍጥ. ፵፮፡፩–፯። ልጆቹን እና ዘሮቻቸውን ባረከ፣ ዘፍጥ. ፵፱። ሞተ፣ ዘፍጥ. ፵፱፡፴፫።

ትእዛዛትን አከበረ፣ እናም ዛሬ ከአብርሐም እና ከይስሐቅ ጋር ወደ ዘለአለማዊነታቸው ገብ ተዋል፣ እና በዙፋናት ተቀምጠዋል፣ ት. እና ቃ. ፲፴፪፡፴፯።

ያዕቆብ፣ የጌታ ወንድም

በአዲስ ኪዳን ውስጥ የጌታ (ገላ. ፩፡፲፱) እና ዮሳ፣ የስምዖን፣ የይሁዳ፣ እና የአንዳንድ እህቶች ወንድም (ማቴ. ፲፫፡፶፭–፶፮፣ ማር. ፮፡፫፣ ይሁዳ ፩፡፩)። እርሱም ትክክለኛው ያዕቆብ ተብሎ ይታ ወቅ ነበር እናም በኢየሩሳሌም ቤተክርስትያን ውስጥ አስፈላጊ ቦታ የያዘም ነበር (የሐዋ. ፲፪፡፲፯፣ ፲፭፡፲፣ ፲፡ ፩ ቆሮ. ፲፭፡፯፣ ገላ. ፪፡ ፱–፲፪)። ምናልባት የያዕቆብ መልእክትን የጻፈው እርሱ ነው።

የያዕቆብ መልእክት፣ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያለ መፅሐፍ። በመጀመሪያ ይህ የተጻፈው በውጪ ለተ በተኑት ለአስራ ሁለቱ የእስራኤል ጎሳዎች ነበር እና የተጻፈውም ምናልባት በኢየሩሳሌም ነበር። መል እክቱ ስለተግባራዊ ሀይማኖት በግልፅ የተጻፉ ነገ ሮች ነበሩት፣ በእዚህም ተጨማሪ በምዕራፍ ፩ ውስጥ ሰው እውቀት ካጣ፣ እግዚአብሔርን ለእ ርዳታ እንዲጠይቅ አስፈላጊ ምክር የሚሰጥም ነበር (ያዕ. ፩፡፭–፮፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፱–፳)። ምዕራፍ ፪ ስለእምነት እና ስራ ይናገራል። ምዕራፍ ፫–፬ ምላስን ስለመቆጣጠር አስፈላጊነት ይናገራሉ እናም ቅዱ ሳን እርስ በራስ ክፉ እንዳይነጋገሩ ይገስጻሉ። ምዕ ራፍ ፭ ቅዱሳን ትእግስት እንዲኖራቸው እና ሲታ መሙ ኸማግሌዎችን ለበረከት እንዲጠሩ ያበረታ ታል፣ ደግሞም ሌሎችን ለመቀየር መርዳት ስላለው በረከት ያስተምራል።

ያፌት። *ደግምም ኖኅ፣ የመፅሐፍ ቅዱስ የአባቶች አለቃ ተመልከቱ*

የብሉይ ኪዳን ነቢይ ኖኅ ታላቅ ልጅ (ሙሴ ፰፡፲፪)።

ኖኅም ያፌትን ወለደ፣ ዘፍጥ. ፭፡፴፪ (ዘፍጥ. ፮፡፲፣ ሙሴ ፰፡፲፪)። ያፌትና ሚስቱ ወደ ኖኅ መር ከብ ገቡ፣ ዘፍጥ. ፯፡፲፣ ያፌትም ከመርከብ ወጣ፣ ዘፍጥ. ፱፡፲፰። እግዚአብሔርም ያፌትን ያስፋ፣ ዘፍጥ. ፱፡፳፯።

ይሁዳ፣ የያዕቆብ ልጅ። *ደግምም መፅሐፍ ቅዱስ፣ አይሁዶች፣ እስራኤል ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የያዕቆብ እና የልያ አራተኛ ወንድ ልጅ (ዘፍጥ. ፳፱፡፴፭፣ ፴፭፡፳፯–፳፯፣ ፴፣ ፡፣ ፡፣ ፡፡)። ያዕቆብ ይሁዳ በያዕቆብ ልጆች መካከል በፍጥረት መሪ እንደሚሆን እና ሴሎ (ኢየሱስ ክርስቶስ) የእርሱ ትውልድ እንደሚሆን ባረከው (ዘፍጥ. ፴፱፡፣)።

የይሁዳ ጎሳ፣ በከነዓን ከሰፈሩ በኋላ የይሁዳ ጎሳ መሪነትን ወሰደ። የእዚህ ዋና ተፎካካሪ ጎሳ የኤፍሬም ጎሳ ነበር። ሙሴ የይሁዳ ጎሳን ባረከ (ዘዳግ. ፴፫፡፯)። ከሰለሞን ዘመነ መንግስት በኋላ፣ የይሁዳ ጎሳ የይሁዳ መንግስት ሆነ።

የይሁዳ መንግስት፣ በሮብዓም ዘመነ መንግስት የሰለሞን ግዛቶች ወደ ሁለት መንግስቶች ተሰበሩ፣ ዋና ምክንያቱም በኤፍሬም እና በይሁዳ ጎሳዎች መካከል በነበረው ቅንዓት ነበር። የደቡብ መንግስት፣ ወይም የይሁዳ መንግስት፣ የይሁዳ ጎሳን እና የቢንያም ታላቅ ክፍልን ያጠቃለለ ነበር። ኢየሩሳሌም ዋና ከተማ ነበረች። ከሰሜን መንግስት በላይ ያህዌይን የሚያመልኩ ታማኞች ነበሩ። ይሁዳ ከሰሜን እና ከምስራቅ መጠቃት እስከዚህም የተጋለጡ አልነበሩም፣ እናም እስከባቢሎን ምርኮ ድረስ ዋነኛው ሀይል በዳዊት ቤተሰብ እጆች ውስጥ ነበር። የይሁዳ መንግስት ብዙ ህዝብ ከነበረው እና ጠካራ ከነበረው ከእስራኤል መንግስት ውድቀት በኋላ ለ፲፴፭ አመት ለመኖር ችሏል።

የይሁዳ በትር፣ ይህም መፅሐፍ ቅዱስን እንደ ይሁዳ ቤት መዝገብ ይጠቁመዋል (ሕዝ. ፴፯፡፲፭–፲፱)። በጓለኛው ቀናት፣ የእስራኤል ቤት ቅርን ጫፎች በሚሰበሰቡበት ጊዜ፣ ቅዱስ መዝገቦቻቸውም አብረው ይሰበሰባሉ። እነዚህ የቅዱሣት መጻህፍት መዝገቦች እርስ በራስ ይረዳዳሉ እናም ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ፣ የእስራኤል አምላክ እና የአለም ሁሉ አምላክ እንደሆነ የአንድነት ምስክርን ይሰራሉ፣ (ጆ.ስ.ት.፣ ዘፍጥ. ፶፡፳፭–፴፮ [ተጨማሪ]፣ ፪ ኔፊ ፫፣ ፳፱)።

ይሁዳ፣ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የይሁዳ መልዕክት ጸሀፊ

በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ ከኢየሱስ ወንድሞች አንዱ እናም ምናልባት የይሁዳ መልእክት ጸሀፊ (ማቴ. ፲፫፡፶፭፣ ይሁዳ ፩፡፩)።

የይሁዳ መልእክት፣ ይህ መፅሐፍ በእምነታቸው እየደከሙ ላሉት ቅዱሳን ይሁዳ የጻፈው ደብዳቤ ያለበት ነው። የሚዳከሙትም በመካከላቸው ክርስትያን ነን የሚሉ ግን በስነ ምግባር ጥሩ ያልሆነው ጣዖት አምላኪ እና የስነምግባር ህግን የሚያከብሩ ምሳሌዎች ነን በሚሉት ነበር። ይሁዳ ስለመንፈሳዊ አደጋ ለማስነቃት እና ታማኝ እንዲሆኑ ለማበረታታት ፈልጎ ነበር።

በይሁዳ መልእክት ውስጥ መጠቀስ ከሚገባቸው ውስጥ አንዳንዶቹ ቁጥር ፮ ውስጥ ስለሰማይ ጦር ነትና ስለሉስፈርና መላዕክቱ ከቅድመ ምድር ህይወት መጣል የሚናገረው (አብር. ፫፡፳፭–፳፰)፣ እና በቁጥር ፲፬–፲፭ ውስጥ በሔኖክ ትንቢትን መጥቀሱ ነበር።

ይሁዳ፣ የያዕቆብ ወንድም

በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ ከመጀመሪያ የኢየሱስ ክርስቶስ አስራ ሁለት ሐዋሪያት አንዱ (ሉቃ. ፮፡፲፫–፲፮)። ምናልባት ልብድዮስ ታዴዎስ ተብሎም ይጠራ ነበር (ማቴ. ፲፡፪–፬)።

ይሳኮር። *ደግምም እስራኤል፣ ያዕቆብ፣ የይስሐቅ ልጅ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ የያዕቆብና የልያ ወንድ ልጅ (ዘፍጥ. ፴፡፲፯–፲፰፣ ፴፭፡፳፫፣ ፴፮፡፲፫)። የእርሱ ትውልዶች ከእስራኤል አስራ ሁለት ጎሳዎች አንዱ ሆነ።

የይሳኮር ጎሳዎች፣ ለይሳኮር የተሰጠው የያዕቆብ በረከት በዘፍጥረት ፴፱፡፲፬–፲፭ ውስጥ ይገኛል። በከነዓን ከሰፈሩ በኋላ፣ ከእስድሬሎን ሜዳ በተጨማሪ እጅግ በጣም ሀብታም የፍልስጥኤምን ምድር ጎሳው ተቀበለ። በይሳኮር ድንበር ውስጥ በአይሁዳ ታሪክ ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ ብዙ ቦታዎች ነበሩ፣ ለምሳሌ፣ ቀርሜሎስ፣ መጊዶ፣ ዶታይን፣ ጊልቦዓ፣ ኢይዝራኤል፣ ታቦር፣ እና ናዝሬት (ኢያ. ፲፱፡፲፯–፳፫)

ይስሐቅ። *ደግምም አብርሐም—የአብርሐም ዘር ተመልከቱ*

የብሉይ ኪዳን የአባቶች አለቃ። በአብርሐም እና ሣራ በሽምግልናቸው መወለዱ ተአምራት ነበር (ዘፍጥ. ፲፭፡፬–፮፣ ፲፯፡፲–፲፭፣ ፳፩፡፩–፳)። አብርሐም ይስሐቅን ለመስዋዕት ማቅረቡ እንደ እግዚአብሔርና እንደ አንድያ ልጁ ምሳሌ ነበር (ያዕቆ. ፪፡፳)። ይስሐቅ ለአብርሐም የተገባው ቃል ኪዳን ወራሽ ነበር (ዘፍጥ. ፳፭፡፱–፲፪፣ ፭ ኔፊ ፲፯፡፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፲)።

ይስሐቅ ተወለደ፣ ዘፍጥ. ፳፭፡፭–፯። በሞሪያ ተራራ እንደ መስዋዕት ሊሰዋ ነበር፣ ዘፍጥ. ፳፪፡፭–፲፱ (ት. እና ቃ. ፲፭፡፱)። አገባ፣ ዘፍጥ. ፳፬። ከልጆቹ ጋር ተነጋገረ፣ ዘፍጥ. ፳፯፡፭–፳፰፡፱።

ከአብርሐምና ከያዕቆብ ጋር ወደ ዘለአለማዊነታቸው ገብቷል፣ ት. እና ቃ. ፲፴፪፡፴፯ (ማቴ. ፳፡፲፭)።

ይሁበኣል። *ደግምም ጌዴዎች (ብሉይ ኪዳን) ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ የበኣልን መሰዊያ ከደመሰሰ በኋላ ለጌዴዎን የተሰጠ ስም (መሳ. ፮፡ ፴፪፤ ፯፡ ፩፤ ፱፤ ፩ ሳሙ. ፲፪፡ ፲፩)።

ይቅርታ ማድረግ። *ደግምም መናዘዝ፤ መጸጸት፣ ንስሀ መግባት፤ የኃጢያት ስርየት፤ የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ ተመልከቱ*

በቅዱሳት መጻህፍት ውስጥ እንደሚጠቀሙበት፣ ይቅርታ ማድረግ ከሁለቱ ነገሮች አንዱ ነው፡ (፩) እግዚአብሔር ሰዎችን ይቅርታ ሲያደርግ፣ ለኃጢ ያት የተመደበውን ቅጣት ይሰርዛል ወይም ያስወ ግዳል። በክርስቶስ የኃጢያት ክፍያ በኩል፣ በመ ግደል ወይም በመንፈስ ቅዱስ ላይ ይቅርታ የሌለ ውን ኃጢያት ከፈጸሙት በስተቀር፣ የኃጢያቶች ስርየት ንስሀ ለሚገቡት በሙሉ ይገኛል። (፪) ሰዎች ለእርስ በራስ ይቅርታ ሲሰጣጡ፣ እርስ በራስ በክ ርስቶስ አይነት ፍቅር ይዋደዳሉ እናም ላስከፉዋቸ ውም ምንም መጥፎ ስሜት አይኖራቸውም (ማቴ. ፭፡ ፵፫–፵፭፤ ፮፡ ፲፪–፲፭፤ ሉቃ. ፲፯፡ ፫–፬፣ ፩ ኔፊ ፯፡ ፲፱–፳፩)።

እግዚአብሔር ታጋሽና ምሕረቱ የበዛ፡ መተላለ ፍን ይቅር የሚል፡ ኃጢአተኞችንም ከቶ፣ ዘኍል. ፲፬፡ ፲፰። ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ፣ ኢሳ. ፩፡ ፲፰።

እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደ ላችንን ይቅር በለን፣ ማቴ. ፮፡ ፲፪ (ሉቃ. ፲፩፡ ፬፣ ፫ ኔፊ ፲፫፡ ፲፩)። ኃጢአትን ያስተሰርይ ዘንድ ለሰው ልጅ ሥልጣን አለው፣ ማቴ. ፱፡ ፮ (ማቴ. ፲፰፡ ፴፭፣ ማር. ፪፡ ፲፡ ሉቃ. ፭፡ ፳–፳፬)። ወንድሜ ቢበድ ለኝ ስንት ጊዜ ልተውለት፣ ማቴ. ፲፰፡ ፳፩–፳፪ (ት. እና ቃ. ፶፰፡ ፶)። በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚ ሳደብ ሁሉ ግን ለዘላለም አይሰረይለትም፣ ማር. ፫፡ ፳፱ (አልማ ፴፱፡ ፮)። ወንድምህ ቢበድልህ ገሥጸው፡ ቢጸጸትም ይቅር በለው፣ ሉቃ. ፲፯፡ ፫። አባት ሆይ፡ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላ ቸው፣ ሉቃ. ፳፫፡ ፴፬።

ይቅር ለመባል ጸልዩ፣ ፩ ኔፊ ፯፡ ፳፩። ለኃጢ አታችን ይቅርታን እናገኝ ዘንድ የክርስቶስን የደም ክፍያ በእኛ ላይ አድርግ፣ ሞዛያ ፬፡ ፪። በእኔና በአ ንተ ፊት ኃጢአቱን ከተናዘዘ፣ እናም ንስሃ ከገባ እር ሱን ይቅር ትለዋለህ፣ ሞዛያ ፳፮፡ ፳፱–፴፩።

፴፪ ሆናም፣ ንስሃ የሚገባ እና የጌታን ትዛዛት የሚያደርግ ይቅር ይባላል፣ ት. እና ቃ. ፩፡ ፴፪። በሙሉ ነፍስህ እጨድ፣ እናም ኃጢያትህ ይቅር ተብሎልሃል፣ ት. እና ቃ. ፴፩፡ ፭ (ት. እና ቃ. ፹፬፡ ፳፩)። ለኃጥያቱ ንስሀ የሚገባም፣ ይቅርታ ይደረግለታል፣ እናም እኔ ጌታ ደግሜ አላስታው ሳቸውም፣ ት. እና ቃ. ፶፰፡ ፶፪። እኔ ጌታ ይቅርታ ልሰጥ ለምፈልገው ይቅርታ እሰጣለሁ፣ ነገር ግን ከእናንተ ለሁሉም ሰዎች ይቅርታ እንድታደርጉ ይጠበቅባችኋል፣ ት. እና ቃ. ፳፬፡ ፲። እርስ በርስ የተላለፋችሁትን ይቅር ከተባባላችሁ፣ እንደዚሁም እኔ ጌታ ይቅር እላችኋለሁ፣ ት. እና ቃ. ፹፪፡ ፩። የምወዳቸውንም ኀጥያታቸውን ለመሰረይ እገስጻ ቸዋለሁ፣ ት. እና ቃ. ፶፭፡ ፩።

ለተላለፍከው ይቅርታ ሰጥቼሀለሁኝ፣ ሙሴ ፮፡ ፶፫።

ይቅርታ የሌለው ኃጢያት። *ደግምም መስደብ፤ መንፈስ ቅዱስ፤ የጥፋት ልጆች፤ ግድያ ተመልከቱ*

መንፈስ ቅዱስን የመካድ ኃጢያት፣ ምህረት ለማግኘት የማይችል ኃጢያት።

መንፈስ ቅዱስን ለሰደበ አይሰረይለትም፣ ማቴ. ፲፪፡ ፴፩–፴፪ (ማር. ፫፡ ፳፱፣ ሉቃ. ፲፪፡ ፣)። ከመ ንፈስ ቅዱስም ተካፋዮች ሆነው የነበሩትን በኋላም የካዱትን እንደገና ለንስሐ እነርሱን ማደስ የማ ይቻል ነው፣ ዕብ. ፮፡ ፬–፮። የእውነትን እውቀት ከተቀበልን በኋላ ወደን ኃጢአት ብናደርግ ከእን ግዲህ ወዲህ ስለ ኃጢአት መሥዋዕት አይቀርል ንም፣ ዕብ. ፣ ፳፯፤

በአንተ ውስጥ ስፍራ የነበረውን መንፈስ ቅዱ ስን የምትክድ ከሆነ፣ እናም እንደካድከው ካወቅህ፣ እነሆ፣ ይህ ይቅር የማይባል ኃጢያት ነው፣ አልማ ፴፱፡ ፭–፮ (ያዕቆ. ፯፡ ፲፱)።

የአብን አንድያ ልጅ ስለካዱት፣ እናም እርሱ ንም በራሳቸው ስለሰቀሉት ይቅርታ የላቸውም፣ ት. እና ቃ. ፷፮፡ ፴–፴፭። መንፈስ ቅዱስን መስደብ ግን አይሰረይለትም፣ በእዚያም አዲስ እና ዘለአለ ማዊ ቃል ኪዳኔን ከተቀበላችሁ በኋላ እናንተ ንጹህ ደም በማፍሰስ የምትገድሉበት ነው፣ ት. እና ቃ. ፲፴፪፡ ፳፮–፳፯።

ይፉ የሆኑ ስራዎች። *ቀኖና ተመልከቱ*

ዮሐንስ፣ የዘብዴዎስ ልጅ። *ደግምም ሐዋሪያ፤ ወንጌሎች፤ የመልከ ጼዴቅ ክህነት፤ የተቀየሩ ሰዎች፤ የዮሐንስ ራዕይ ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከነበሩት አስራ ሁለት ሐዋ ሪያት አንዱ፣ የዘብዴዎስ ልጅ፣ እና የያዕቆብ ወን ድም። በመጀመሪያው ህይወቱ አሳ አጥማጅ ነበር (ማር. ፩፡ ፲፯–፳)። ምናልባት በዮሐ. ፩፡ ፴ ውስጥ የተጠቀሰው ስሙ ያልተነገረው የመጥምቁ ዮሐ ንስ ደቀ መዛሙርት ነው። በኋላም የኢየሱስ ክርስ ቶስ ደቀ መዛሙርት እንዲሆን ጥሪ ተቀበለ (ማቴ. ፬፡ ፳፩–፳፪፤ ሉቃ. ፭፡ ፩–፲፩)። የዮሐንስ ወንጌ ልን፣ ሶስት መልእክቶችን፣ እና የዮሐንስ ራዕይን ፅፏል። የኢያኢሮስ ሴት ልጅ ከሞት በተነሳችበት

ጊዜ (ማር. ፮፡፴–፴፪)፣ በመለወጫ ተራራ ላይ (ማቴ. ፲፯፡፩–፱)፣ እና በጌቴሴማኒ ውስጥ (ማቴ. ፳፮፡፴–፴፮) ከጌታ ጋር ከነበሩት ሶስቱ አንዱ ነበር። በፅሁፉም ውስጥ ስለራሱ በኢየሱስ እንደ ተወደደ ደቀ መዛሙርት (ዮሐ. ፲፫፡፳፫፣ ፳፩፡፳) እና እንደ “ሌላው ደቀ መዛሙርት” (ዮሐ. ፳፡፪–፳) ተናግሯል። ኢየሱስ እርሱንና ወንድሙን ቦአኔርጌስ ብሎ ሰየማቸው፡ የነጎድጓድ ልጆች ማለት ነው (ማር. ፫፡፲፯)። በስቅለት እና ትንሳኤ ታሪክ ውስጥ እርሱ ብዙ ጊዜ ተጠቅሷል (ሉቃ. ፳፪፡፰፣ ዮሐ. ፲፰፡፲፭፣ ፲፱፡፳፮–፳፯፣ ፳፡፪–፰፣ ፳፩፡፩–፪)። ዮሐንስ ወደ ፍጥሞ ተወገደ፣ በእዚያም የዮሐንስ ራዕይን ጻፈ (ራዕ. ፩፡፱)።

በኋለኛው ቀን ራዕይ ውስጥም ዮሐንስ ተደጋግሞ ተጠቅሷል (፩ ኔፊ ፲፬፡፲፰–፳፯፣ ፫ ኔፊ ፳፰፡፲፣ ኤተር ፬፡፲፯፣ ት. እና ቃ. ፯፣ ፳፯፡፲፪፣ ፳፩፡፲፬፣ ፳፡፲፣ ፹፰፡፲፣ ፹፱፡፲–፳፩)። እነዚህ ምንባቦች የዮሐንስን የመፅሐፍ ቅዱስ መዝገብን ያረጋግጣል እናም ስለእርሱ ታላቅነት እና በብሉይ ኪዳን ዘመናት እና በመጨረሻው ቀናት በምድር ላይ እንዲያከናውን ጌታ ስለሰጠው ስራ አስፈላጊነት አስተያየት ይሰጣሉ። የኋለኛው ቀን ቅዱሣት መጻህፍት ዮሐንስ እንዳልሞተ ነገር ግን እስከ ጌታ ዳግም ምፅዓት ድረስ በምድር እንደአገልጋይ እንዲቆይ እንደተፈቀደለት ግልፅ ያደርጋሉ (ዮሐ. ፳፩፡፳–፳፫፣ ፫ ኔፊ ፳፰፡፲–፣ ት. እና ቃ. ፯)።

የዮሐንስ መልእክቶች፣ ምንም እንኳን የእነዚህ ሶስት መልእክቶች ጸሀፊ እራሱን በስም ባይጠቅ ስም፣ ቋንቋው የሐዋሪያው ዮሐንስ ፅሁፍ ጋር በጣም የተመሳሰሉ ስለሆኑ እርሱ ሶስቱንም እንደጻፋቸው ይገመታል።

፩ ዮሐንስ ፩ ቅዱሳን ከእግዚአብሔር ጋር ጓደኝነትን እንዲያገኙ ይገስጻል። ምዕራፍ ፪ ቅዱሳን እግዚአብሔርን በታዛዥነት እንዲያውቁት ትኩረት ይሰጣል እናም አለምን እንዳያፈቅሩ ያስተምራል። ምዕራፍ ፫ ሁሉም የእግዚአብሔር ልጆች እንዲሆኑ እና እርስ በራስ እንዲዋደዱ ጥሪ ይሰጣል። ምዕራፍ ፬ እግዚአብሔር ፍቅር እንደሆነ እና በሚያፈቅሩት ውስጥ እንደሚኖር ይገልጻል። ምዕራፍ ፭ ቅዱሳን በክርስቶስ እምነት በኩል በእግዚአብሔር እንደተ ወለዱ ይገልጻል።

፪ ዮሐንስ ከ፩ ዮሐንስ ጋር አንድ አይነት ነው። በእዚህም “በምርጥ ሴቷ” ልጆች ታማኝነት ምክ ንያት ተደሰተ።

፫ ዮሐንስ ጋይዮስ የሚባልን ሰው ለታማኝነቱ እና እውነቱን ለሚያፈቅሩት ለሰጠው እርዳታ ያሞ ግሳል።

የዮሐንስ ወንጌል፣ በእዚህ የአዲስ ኪዳን መፅሐፍ ውስጥ፣ ሐዋሪያው ዮሐንስ (፩) ኢየ ሱስ እርሱ ክርስቶስ ወይም መሲህ እንደሆነ እና (፪) ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ መሰ ከረ (ዮሐ. ፳፡፴፩)። የሚገልጻቸው የኢየሱስ ህይ ወቶች በጥንቃቄ የተመረጡ ናቸው እናም በዚህ አላማም የተዘጋጁ ነበሩ። መፅሐፉ የሚጀምረው ክርስቶስ በቅድመ ምድር ህይወት ስለነበረው ስል ጣን መግለጫ ነው፡ እርሱም ከእግዚአብሔር ጋር ነበር፣ እርሱም እግዚአብሔር ነበር፣ እናም እርሱ የሁሉም ነገሮች ፈጣሪ ነበር። በስጋ እንደ አብ አን ድያ ልጅ የተወለደ ነበር። ዮሐንስ የእርሱን መለኮ ታዊነት እና ከሞት መነሳቱን ታላቅ አፅንዖት በመ ስጠት የኢየሱስ አገልግሎት መንገድን ይከታተ ላል። ኢየሱስ በተአምራት፣ በምስክሮች፣ በነ ቢያት፣ እና በክርስቶስ በእራሱ ድምፅ እንደተ መሰከረው የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ በግልፅ ያረጋግጣል። ዮሐንስ ብርሀንንና ጨለማን፣ እው ነትንና ስህተትን፣ ጥሩንና ክፉን፣ እግዚአብሔር ንና ዲያብሎስን በማነጻጸር ያስተምራል። ምናል ባት ስለኢየሱስ ቅዱስነት እና ስለአይሁድ መሪ ዎች እምነተ ቢስነት በግልፅ የሚገልፅ ሌላ ምንም መዝገብ የለም።

ዮሐንስ ስለክርስቶስ የይሁዳ አገልግሎት፣ በልዩም ስለስጋዊ አገልግሎቱ የመጨረሻ ሳም ንት፣ ሲፅፍ፣ ዋና ጽሁፋቸው ማቴዎስ፣ ማር ቆስ፣ እና ሉቃስ ስለገሊላ አገልግሎቱ ነበር። ከዚህ ወንጌል ብዙዎቹ በኋለኛው ቀን ራዕይ ተገልጸዋል (ት. እና ቃ. ፯ እና ት. እና ቃ. ፹፰፡፲–፲፯)።

በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የተገለጹትን የአዳኝ ህይወት ድርጊቶችዝርዝር፣ የወንጌሎች ስምምነ ትን ተመልከቱ።

ለራዕይ መፅሐፍ፣ የዮሐንስ ራዕይ ተመልከቱ

ዮሴፍ፣ የማርያም ባለቤት። *ደግሞም* *ማርያም፣ የኢየሱስ እናት፣ ኢየሱስ ክርስቶስ* *ተመልከቱ*

የኢየሱስ እናት ማርያም ባለቤት። ዮሴፍ የዳዊት ዘር (ማቴ. ፩፡፩–፲፮፣ ሉቃ. ፫፡፳፫–፴፰) እናም በናዝሬት ይኖር ነበር። ከማርያም ጋር የተዳረ ነበር። ከጋብቻቸው በፊት፣ ማርያም የአዳኝ እናት እን ድትሆን እንደተመረጠች ባስታወቃት በመልአኩ ገብርኤል ማርያም ተነበየች (ሉቃ. ፩፡፳፯–፴፭)። ዮሴፍ ስለዚህ መለኮታዊ ውልደት ራዕይን ተቀበለ (ማቴ. ፩፡፳–፳፭)።

ማርያም የኢየሱስ ብቸኛ ወላጅ ነበረች ምክን ያቱም እግዚአብሔር የኢየሱስ አባት ነውና። ነገር ግን አይሁዶች ዮሴፍን እንደ ኢየሱስ አባት ያስ ቡት ነበር፣ ኢየሱስንም እንደዚህ ነበር የሚያስቡት (ሉቃ. ፪፡፴፫፣ ፴፩)። በሰማያዊ ህልሞች ማስጠ ንቀቂያ በመቀበል፣ ዮሴፍ የህጻን ኢየሱስን ህይ ወት ወደ ግብፅ በመሸሽ አዳነ (ማቴ. ፪፡፲፫–፲፭)። ሄሮድስ ከሞተ በኋላ፣ መልአክ ዮሴፍ ኢየሱስን

ወደ እስራኤል እንዲወስድ መመሪያ ሰጠው (ማቴ. ፪፡፲፬–፳፫)።

ዮሴፍ፣ የያዕቆብ ልጅ። *ደግምም እስራኤል፤ ያዕቆብ፣ የይስሐቅ ልጅ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የያዕቆብ እና የራሔል በኩር ልጅ (ዘፍጥ. ፴፡፳፪–፳፬፣ ፴፯፡፫)።

ዮሴፍ የበኩር መብትን ያገኘው ከያዕቆብ የመ ጀመሪያ ባለቤት በኩል ልጅ ሮቤል መብቱን በመ ተላለፉ ምክንያት ስላጣ ነበር (፩ ዜና ፭፡፩–፪)። እርሱ ብቁ ስለነበረ፣ ዮሴፍ እንደ ያዕቆብ ሁለ ተኛ ባለቤት በኩል ልጅ፣ ለበረከቱ በተከታይነት መብት ነበረው። ያዕቆብ ከመሞቱ ከትንሽ ጊዜ በፊት፣ ዮሴፍ ከአባቱም በረከትን ተቀበለ (ዘፍጥ. ፵፱፡፳፪–፳፮)።

ዮሴፍ ታላቅ መንፈሰ ጠንካራነት ያለው፣ “ያለ ብልህ አዋቂም ሰው” ነበር (ዘፍጥ. ፵፩፡፴፱)። የጲጥፋራ ባለቤትን ማስወገዱ የእምነት፣ የንጹህነት እና የግለሰብ ታማኝነት ምሳሌ ነው (ዘፍጥ. ፴፱፡፭–፲፪)። በግብፅ ውስጥ፣ ጆሴፍ እውነተኛ ማንነቱን ለወንድሞቹ ሲገልፅ፣ ምንም ላደረጉበት እነርሱን ሳይወቅስ ምስጋና ሰጣቸው። ስራቸው የእግዚአ ብሔርን ፍቃድ ለማሟላት እንደረዳ አምኖ ነበር (ዘፍጥ. ፵፭፡፬–፲፭)።

የኋለኛው ቀን ራዕይ የጆሴፍ ቤተሰብ በኋለኛው ቀን ስላላቸው ታላቅ ተልዕኮ ገልጦአል (ጆ.ስ.ት.፣ ዘፍጥ. ፶፡፳፬–፴፯ [ተጨማሪ]፤ ፪ ኔፊ ፫፡፫–፳፪፤ ፫ ኔፊ ፳፡፳፭–፳፯)።

እስራኤልም ዮሴፍን በጣም ይወደው ነበር እናም በብዙ ኀብር ያጌጠችም ቀሚስ አደረገለት፣ ዘፍጥ. ፴፯፡፫። በቅንአት ምክንያት የዮሴፍ ወንድሞች እርሱን መጥላት ጀመሩ እና ሊገድሉትም አቀዱ፣ ነገር ግን በዚህ ምትክ ወደ ግብጽ እየተጓዙ ለነበሩ ነጋዴዎች ሸጡት፣ ዘፍጥ. ፴፯፡፭–፴፯፤ በግብጽ ውስጥ፣ ጌታ ዮሴፍን አበለጸገ እናም በጲጥፋራ ቤት ውስጥ ገዢ ሆነ፣ ዘፍጥ. ፴፱፡፩–፱። የጲጥፋራ ባለ ቤት ዮሴፍ ሊያስተኝ ሞከረ በማለት ዋሸች፣ ዮሴፍ በስህተት ተኮነነ እናም ታሰረ፣ ዘፍጥ. ፴፱፡፲–፳። ዮሴፍ የፈርዖን የጠጅ አሳላፊዎቹ አለቃንና የእን ጀራ አበዛዎቹ አለቃን ህልሞች ተረጎመ፣ ዘፍጥ. ፵። ዮሴፍ ከፈርዖን ህልሞች አንዱን ስለተረጎመ፣ ፈርዖን ዮሴፍን ወደደው፣ ዮሴፍን በግብጽ ሁሉ ገዢ አደረገው፣ ዘፍጥ. ፵፩፡፲፩–፵፩። ኤፍሬምና ምናሴ ተወለዱ፣ ዘፍጥ. ፵፩፡፶–፶፪። ዮሴፍ ከወ ንድሞቹና ከአባቱ ጋር እንደገና ተገናኘ፣ ዘፍጥ. ፵፭–፵፮። በ፲፯ አመቱ ዮሴፍ በግብጽ ውስጥ ሞተ፣ ዘፍጥ. ፶፡፳፮–፳፮።

ዮሴፍ፣ የዮሴፍ በትር። *መፅሐፈ ሞርሞን፤ ኤፍሬም—የዮሴፍ ወይም የኤፍሬም በትር ተመልከቱ*

ዮቶር። *ደግምም ሙሴ ተመልከቱ*

ሙሴ ከግብፅ ከሸሸ በኋላ ለሙሴ ቤት የሰጠው የብሉይ ኪዳን ልዑል እና የምድያም ካህን። ራጉ ኤል ተብሎም ይጠራል (ዘፀአ. ፪፡፲፰)። በኋ ላም ሙሴ የዮቶርን ሴት ልጅ ሲፓራ አገባ (ዘፀአ. ፫፡፩፣ ፬፡፲፰፣ ፲፰፡፩–፲፪)። ዮቶር ሙሴን ሀላፊ ነቱን እንዲያካፍል አስተማረው፣ (ዘፀአ. ፲፰፡፲፫–፳፯)። ሙሴ የመልከ ጼዴቅ ክህነትን ከዮቶር ተቀ በለ፣ (ት. እና ቃ. ፹፬፡፲–፲፯)።

ዮናስ። *ደግምም ነነዌ ተመልከቱ*

በጌታ ለነነዌ ከተማ ንስሀ መግባት እንዲሰብክ የተጠራ የብሉይ ኪዳን ነቢይ (ዮና. ፩፡፩–፪)።

ትንቢተ ዮናስ፣ ስለዮናስ ህይወት አጋጣሚ የሚ ናገር የብሉይ ኪዳን መፅሐፍ። ምናልባት ዮናስ ይህን መፅሐፍን አልጻፈም ነበር። የትንቢተ ዮናስ ዋናው ሀሳብ ያህዌህ በማንኛውም ቦታ እንደሚነግስ እና ፍቅሩን ለአንድ ሀገር ወይም ህዝብ የሚገድብ አይ ደለም።

በምዕራፍ ፩ ውስጥ፣ ጌታ ዮናስን በነነዌ እንዲ ሰብክ ጠራው። ጌታ እንዳዘዘው በማድረግ፣ ዮናስ በመርከብ ሸሸ እናም በትልቅ አሳ ተዋጠ። በምዕ ራፍ ፪ ውስጥ፣ ዮናስ ወደ ጌታ ጸለየ፣ እና አሳው በድርቅ ምድር ላይ ዮናስን ተፋው። ምዕራፍ ፫ ዮናስ ወደ ነነዌ እንደሄደ እና የዚህን ውድቀት እንደተነበየ ይመዘግባል። ነገር ግን፣ ህዝቡ ንስሀ ገባ። ምዕራፍ ፬፣ ጌታ ህዝብን ስላዳነ በመናደዱ ጌታ ዮናስን ገሰጸ።

የዮናስ በአሳ መዋጡ እንደ ኢየሱስ ሞት እና ትን ሳኤ አስቀድሞ የሚነግር እንደሆነ ኢየሱስ አስተማረ (ማቴ. ፲፪፡፴፱–፵፣ ፲፮፡፩፣ ሉቃ. ፲፩፡፳፱–፴)።

ዮናታን። *ደግምም ሳያል፣ የእስራኤል ንጉስ፤ ዳዊት ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የእስራኤል ንጉስ የሳያል ልጅ። ዮናታን የዳዊት የቅርብ ጓደኛ ነበር (፩ ሳሙ. ፲፰–፳፣ ፴፩)።

ደሀ። *ደግምም ምፅዋት፣ የምፅዋት ስጦታ፤ በኩራት፣ በጎ ድርጊት፤ ትሁት፣ ትሕትና፤ ጾም፣ መጾም ተመልከቱ*

በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ፣ *ደሀ* (፩) እንደ ምግብ፣ ልብስ፣ እና መጠለያ አይነት አስፈላጊ ነገሮች የሌላቸውን ሰዎች፣ ወይም (፪) ትሁት እና ትዕቢት የሌላቸው ሰዎችን ይጠቁማል።

በአለማዊ እቃዎች ደሀነት፣ በድሀው ወንድምህ ላይ እጅህን አትጨብጥ፣ ዘዳግ. ፲፭፡፯። በጎጢ አተኛ ትዕቢት ድሀ ይናደዳል፣ መዝ. ፲፡፪። ለድሀ የሚሰጥ አያጣም፣ ምሳ. ፳፰፡፳፯። ድሆች ወደ ቤትህ አስገባ፣ ኢሳ. ፶፰፡፯–፰።

ፍጹም ልትሆን ብትወድ፥ ለድሆች ስጥ፤ ማቴ. ፲፱፡፳፩ (ማር. ፲፡፳፩፣ ሉቃ. ፲፰፡፳፪)። እግዚአ ብሔር የዚህን ዓለም ድሆች አልመረጠምን፣ ያዕ. ፪፡፭።

ሀብታም በመሆናቸው ድሆችን ይጠላሉ፣ ፤ ኤፌ ፬፡፴። ለኃጢአታችሁ ስርየትን እንድታገኙ የራ ሳችሁን ነገር ለድሃ ስጡ፣ ሞዛያ ፬፡፳፯። ለድሆች ከቁሳቁሶቻቸው አካፈሉ፣ አልማ ፭፡፳፯። የተቸገ ሩትን ካልረዳችሁ፣ ፀሎታችሁ ከንቱ ነው፣ አልማ ፴፬፡፳፰። ኔፋውያን ሁሉም ነገሮች በጋራ ነበሩአ ቸው፣ ፤ ኤፌ ፭፡፲።

ድሆችን ታስታውሳላችሁ፣ ት. እና ቃ. ፵፪፡፴ (ት. እና ቃ. ፵፪፡፴)። ልባችሁ ያልተሰበሩ ድሀ ሰዎ ችም ወዮላችሁ፣ ት. እና ቃ. ፹፯፡፲፯–፲፰። ድሀው ወደ በጉ ጋብቻ ይመጣሉ፣ ት. እና ቃ. ፹፰፡፯–፲፩። ኤጲስ ቆጶሱ የደሀዎችን ፍላጎት ለመርዳት መጓዝ ይገባዋል፣ ት. እና ቃ. ፹፱፡፲፲፪። ድሀዎችን መንከ ባከብ የወንጌል ህግ ይመራል፣ ት. እና ቃ. ፹፩፡፲፯–፲፰።

በመካከላቸውም ማንም ድሀ አልነበረም፣ ሙሴ ፯፡፲፰።

በመንፈስ ደሀነት፣ በድህነት ምክንያት ሳይገደዱ እራሳቸውን ትሁት የሚያደርጉ ከሌሎች በላይ የተ ባረኩ ናቸው፣ አልማ ፴፪፡፩–፯፣ ፲፪–፲፯። በመ ንፈስ ድሆች የሆኑ ወደ እኔም የሚመጡ ብፁአን ናቸው፣ ፤ ኤፌ ፲፪፡፲ (ማቴ. ፭፡፲)።

ለድሆች እና ትሁቶች ወንጌል ይሰበክላቸዋል፣ ት. እና ቃ. ፴፭፡፲፭።

ደህንነት። *ደግሞም መንፈሳዊ ሞት፤ ስጋዊ ሞት፤ ቤዛ፣ ማዳን፣ ቤዛነት፤ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ ከፍተኛነት፤ የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ፤ የቤዛነት ዕቅድ፤ ጸጋ ተመልከቱ*

ከስጋዊ እና መንፈሳዊ ሞት መዳን። ሁሉም ሰዎች ከስጋዊ ሞት በእግዚአብሔር ጸጋ፣ በኢየሱስ ክርስ ቶስ ሞት እና ትንሳኤ በኩል፣ ይድናሉ። ደግሞም እያንዳንዱ ግለሰብ ከመንፈስ ሞት በኢየሱስ ክር ስቶ በማመን፣ በእግዚአብሔር ጸጋ ለመዳንም ይች ላሉ። ይህም እምነት የሚገለጸው በህግጋትና በወን ጌል ስነስርዓቶች ታዛዥ በሆነ ህይወት እና ክርስቶ ስን በማገልገል ነው።

እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው፣ መዝ. ፳፯፡፩። እርሱ አምላኬ መድኃኒቴም ነው፣ መዝ. ፳፪፡፪።

በወንጌል የሚያድን የእግዚአብሔር ኃይል ነው፣ ሮሜ ፩፡፲፮ (ት. እና ቃ. ፳፯፡፱)። የራሳ ችሁን መዳን ፈጽሙ፣ ፊልጵ. ፪፡፲፪። እግዚአብ ሔር በመንፈስ መቀደስ ለመዳን መርጦአችኋል፣ ፤ ተሰ. ፪፡፲፫።

ደህንነትም ነፃ ነው፣ ፤ ኤፌ ፪፡፱።

ከደህንነት በላይ የሆነ ምንም ስጦታ የለም፣ ት. እና ቃ. ፯፡፲፫።

ደህንነት ለመምጣት የሚያስችለው የኢየሱስ ክር ስቶስ ስም ነው፣ ሙሴ ፯፡፶፪ (የሐዋ. ፬፡፲–፲፪)። የሰው ዘሮች ሁሉ በክርስቶስ ኃጢያት ክፍያ በኩል መዳን እንደሚችሉ እናምናለን፣ ኢ.ኢ. ፭፡፲።

የልጆች ደህንነት፣ እንደ ሕፃናትም ካልሆና ችሁ፥ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም፣ ማቴ. ፲፰፡፫።

ትናንሽ ልጆች ዘለዓለማዊ ህይወት ይኖራቸዋል፣ ሞዛያ ፲፭፡፳፭። የህጻን ጥምቀት እርኩሰት ነው፣ እናም ትንሽ ልጆች በኃጢያት ክፍያ ምክንያት በክ ርስቶስ ህያው ናቸው፣ ሞሮኒ ፰፡፰–፳፪። ህጻናት ከአለም መጀመሪያ ጀምሮ በእንድያ ልጄ ድነዋል፤ ለመፈተን ሰይጣን ሃይል አልተሰጠውም፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፴፯–፴፱። ልጆች ወንጌልን ይማሩ እና በስምንት አመታቸው ይጠመቁ፣ ት. እና ቃ. ፳፰፡፲፭–፲፰። በኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢያት ክፍያ በኩል ትንሽ ልጆች የተቀደሱ ናቸው፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፯። ሰዎችም እንደገና በህጻንነት በእግዚአብ ሔር ፊት የዋህ ሆኑ፣ ት. እና ቃ. ፹፫፡፴፰። በተ ጠያቂነት እድሜዎች ከመድረሳቸው በፊት የሞቱ ትን ልጆች ሁሉ በሰለስቲያል መንግስት ውስጥ ድነ ዋል፣ ት. እና ቃ. ፲፴፯፡፲። ልጆች ከአለም መሰረት ጊዜ ጀምሮ ከኀጥያት ንጹህ ናቸው፣ ሙሴ ፯፡፶፭።

ደሊላ። *ደግሞም ፍልስጤማውያን ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሶምሶንን ያታለለችና የካደች ፍልስጤማውያን ሴት፣ (መሳ. ፲፮)።

ደማስቆ

የሶርያ የጥንት ከተማ።

ደማስቆ በበረሀ ዳርቻ የምትገኝ እናም በባራዳ ወንዝ በደንብ የምትጠጣ የለማች መሬት ናት። በቅ ዱሣት መጻህፍት ውስጥ በተደጋጋሚ የምትጠቀስ ናት (ዘፍጥ. ፲፬፡፲፭ ጀምሮ)። ከሞት የተነሳው ጌታ ለጳውሎስ ሲገለፅለት ወደ ደማስቆ እየተጓዘ ነበር (የሐዋ. ፱፡፩–፳፯፣ ፳፪፡፭–፲፯፣ ፳፮፡፲፪–፳)።

ደም። *ደግሞም መስዋዕት፤ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ ተመልከቱ*

በጥንት እስራኤላውያን እና ዛሬም በብዙ ባህ ሎች እንደ ህይወት መቀመጫ ወይም የስጋ በሙሉ በጣም አስፈላጊ ሀይል እንደሆነ ይታያል። በብሉይ ኪዳን ጊዜዎች ውስጥ ጌታ እስራኤላውያንን ደምን እንደምግብ እንዳይበሉ ከለከላቸው (ዘሌዋ. ፫፡፲፯፣ ፯፡፳፮–፳፯፣ ፲፯፡፲–፲፩)።

የመስዋዕት የኃጢያት ዋጋ መክፈያ ሀይል

ያለው በደም ውስጥ ነበር ምክንያቱም ደም ለህይ ወት በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ስለሚታሰብበታል። በብሉይ ኪዳን ውስጥ የነበረው የእንስሳት መስዋዕት በኋላ ኢየሱስ የሚፈፅመው ታላቅ መስዋዕት ምስሌ ነበር (ዘሌዋ. ፲፯፡፲፩፤ ሙሴ ፮፡፮–፯)። የኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢያት ክፍያ ደም ንስሀ የሚገባውን ያጸዳል (፩ ዮሐ. ፩፡፯)።

ወዙም በምድር ላይ እንደሚወርድ እንደ ደም ነጠብጣብ ነበረ፣ ሉቃ. ፳፪፡፴፬። በክርስቶስ ደም መፍሰስ እኛም ተቀድሰናል፣ ዕብ. ፲፡፩–፳፪።

ደሙም ከእያንዳንዱ የሰውነቱ ቀዳዳ ይፈሳል፣ ሞዛያ ፫፡፯ (ት. እና ቃ. ፲፱፡፲፰)።

የጌታ ደም ለኃጢያቶች ስርየት ፈሰሶ ነበር፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፪። የሀጢያት ክፍያን የእራሱን ደም በማፍሰስ አከናወነ፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፳፱።

በደም ነፅተሀል፣ ሙሴ ፯፡፳።

ደም ማፍሰስ። ግድያ ተመልከቱ

ደስታ። *ደግሞም ታዛዥነት፣ ታዛዥ፣ መታዘዝ ተመልከቱ*

በጻድቅ ህይወት የሚመጣ ታላቅ ደስታ። የስጋዊ ህይወት አላማ ሁሉም ሰዎች ደስታ እንዲኖራቸው ነው (፪ ኔፊ ፪፡፳፪–፳፭)። ሙሉ ደስታ የሚመ ጣው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነው (ዮሐ. ፲፭፡፲፩፤ ት. እና ቃ. ፶፫፡፴፫–፴፴፤ ፲፭፡፴፯)።

የዋሃን ደስታቸውን በእግዚአብሔር ያበዛሉ፣ ኢሳ. ፳፱፡፲፱ (፪ ኔፊ ፳፯፡፴)።

ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁ፣ ሉቃ. ፪፡፲። ደስታችሁንም የሚወስድባችሁ የለም፣ ዮሐ. ፲፮፡፳፪። የመንፈስ ፍሬ ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም ነው፣ ገላ. ፭፡፳፪።

ይህም ፍሬ ነፍሴን በደስታ ሞላው፣ ፩ ኔፊ ፰፡፲፪። ሰዎች የሚኖሩትም ደስታም እንዲኖራ ቸው ዘንድ ነው፣ ፪ ኔፊ ፪፡፳፭። የፃድቃን ደስታ ለዘለዓለም ሙሉ ይሆናል፣ ፪ ኔፊ ፱፡፲፰። ለዘለአ ለም በማያልቀው ደስታ ከእግዚአብሔር ጋር ይኖ ራሉ፣ ሞዛያ ፪፡፴፩። ያለኝን ሁሉ እተዋለሁ፣ . . . ይህን ታላቁን ደስታም እቀበል ዘንድ. . .፣ አልማ ፳፪፡፲፭። ምናልባት ጥቂት ነፍሳትን ወደ ንስሃው በማምጣት በእግዚአብሔር እጅ መሳሪያ እሆን ዘንድ በዚህ እመካለሁ፤ እናም ይህም የእኔ ደስታ ነው፣ አልማ ፳፱፡፱። እንዴት ያለ ደስታ ተሰማኝ፤ እናም ምን ዓይነት አስደናቂ ብርሃንን አይቻለሁ፣ አልማ ፴፯፡፳።

ነፍስህን በደስታ የሚሞላ፣ ከመንፈሴ ለአንተ እሰጥሃለው፣ ት. እና ቃ. ፲፩፡፲፫። አንድም ነፍስም ቢሆን እንኳን ወደ እኔ ብታመጡ፣ በአባቴ መንግ ስት ከእርሱ ጋር ደስታችሁ እንዴት ታላቅ ይሆ ናል፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፲፩–፲፯። በዚህ አለም ደስ ታችሁ ሙሉ አይደለምና፣ ነገር ግን በእኔ ደስታችሁ ሙላት አለው፣ ት. እና ቃ. ፲፩፡፴፯።

በዚህ ህይወትም ደስታ ይኖረኛል፣ ሙሴ ፮፡፲–፲፩።

ደቀ መዛሙርት። *ደግሞም ሐዋሪያ፤ መቀየር፣ የተቀየረ፤ ቀንበር፤ ክርስቲያኖች ተመልከቱ*

ክርስቶስ ባስተማረው መሰረት የሚኖር የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታይ (ት. እና ቃ. ፴፩፡፭)። *ደቀ መዛ ሙርት* ኢየሱስ በስጋዊ አገልግሎቱ ጊዜ የጠራቸ ውን አስራ ሁለት ሐዋሪያትን ለመግለፅ ተጠቅመ ውበታል (ማቴ. ፲፡፩–፱)። *ደቀ መዛሙርትም* በኔፋ ውያንና በላማናውያን መካከል ቤተክርስቲያኑን እን ዲመሩ ኢየሱስ የመረጣቸውን አስራ ሁለት ወንዶ ችን ለመግለፅም ተጠቅመውበታል (፫ ኔፊ ፲፱፡፱)።

በደቀ መዛሙርቶቼም መካከል ሕጉን አትም፣ ኢሳ. ፰፡፲፮።

እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀ መዛሙ ርቴ ናችሁ፣ ዮሐ. ፰፡፴፩።

ሞርሞን የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ነበር፣ ፫ ኔፊ ፭፡፲፪–፲፫። እናንተ የእኔ ደቀመዛ ሙርት ናችሁ፣ ፫ ኔፊ ፲፭፡፲፪። ሶስቱ ደቀ መዛ ሙርት ሞትን አይቀምሱም፣ ፫ ኔፊ ፳፰፡፱–፲።

እኔ በመረጥኳቸው ደቀመዛሙርቶቼ አፍ፣ የማስጠንቀቂያው ድምጽ ይሆናል፣ ት. እና ቃ. ፩፡፱። ደቀ መዛሙርቴ በተቀደሰ ቦታ ላይ ይቆ ማሉ፣ ት. እና ቃ. ፴፭፡፴፪። በሁሉም ነገሮችም ድህውን እና ችግረኛውን፣ የታመመውን እና የተ ሰቃየውን የማያስታውሱ ደቀ መዛሙርቴ አይደ ለም፣ ት. እና ቃ. ፹፪፡፴። ለእኔ ህይወቱን ለመስ ጠት ፈቃደኛ ያልሆነውም ደቀመዛሙርቴ አይደ ለም፣ ት. እና ቃ. ፹፫፡፳፯–፳፰።

ደብረ ዘይት ተራራ። *ደግሞም ጌቴሴማኒ ተመልከቱ*

በቁድሮንን ፈፋ በምስራቅ ኮረብታ፣ በምስራቅ ኢየሩሳሌም የሚገኝ ቦታ። በምዕራቡ ዳገት፣ በኮ ረብታው በታች የጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ ይገ ኛል። ቤተ ፋጌ እና ቢታንያ በኮረብታው ጫፍ እና በምስራቅ ዳገታ ላይ ይገኛሉ። ይህ ተራራ የብዙ የመፅሐፍ ቅዱስ ድርጊቶች የተደረጉበት ቦታ ነው (ማቴ. ፳፩፡፫) እናም በኋለኛው ቀን ለሚደርሱት ድርጊቶችም አስፈላጊ ቦታ ነው (ዘካ. ፲፬፡፫–፭፤ ት. እና ቃ. ፴፭፡፴፳–፴፱፤ ፲፴፫፡፳)።

ደካማነት። *ደግሞም ትሁት፣ ትሕትና ተመልከቱ*

ስጋዊ መሆን እናም ችሎታ፣ ጥንካሬ፣ ወይም ብቃት ማጣት። ደካማነት የመሆን ሁኔታ ነው። ሁሉም ሰዎች ደካማ ናቸው፣ እናም ጻድቅ ስራ ለመስራት ሀይል የሚቀበሉት በእግዚአብሔር ጸጋ

ብቻ ነው (ያዕቆ. ፤፡–፯)። ይህም ደካማነት የሚ ታየው በክፍል በግለሰብ ደካማነት ወይም እያንዳ ንዱ ሰው ባለው የጥንካሬ ደካማነት ነው።

የደከሙትን እጆች አበርቱ፣ ኢሳ. ፴፭፡፫–፬። መንፈስስ ተዘጋጅታለች ሥጋ ግን ደካማ ነው፣ ማቴ. ፳፮፡፴፩ (ማር. ፲፬፡፴፰)።

በስጋ መሰረት በውስጤ ባለው ደካማነት ራሴ አመካኛለሁ፣ ፮ ኔፊ ፲፱፡፮። ምንም እንኳን ደካማ ብሆንም እነዚህን ነገሮች እንድፅፍ በእርሱ ታዘዝኩ፣ ፪ ኔፊ ፴፫፡፲፩። አገልጋይህ በፊትህ ደካማ በመሆኑ አትቆጣው፣ ኤተር ፫፡፪። ስንፅፍ ደካሞች በመሆ ናችን አህዛብ ይሳለቁብናል፣ ኤተር ፲፪፡፳፫–፳፭፣ ፴። ድካማቸውን አሳያቸዋለሁ፣ ኤተር ፲፪፡፳፯–፳፱። ድካምህን በማየትህ ጠንካራ ትደረጋለህ፣ ኤተር ፲፪፡፴፯።

ከዚህ በኋላ ከእናንተ መካከል ደካማ የሆነውም ጠንካራ ይሆናል፣ ት. እና ቃ. ፶፣ ፲፯። ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ድክመትን ያውቃል፣ ት. እና ቃ. ፳፪፡፩።

ደዘረት፣ ደግምም ያሬዳውያን ተመልከቱ

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ በትርጉም የንብ ቀፎ የሚባለውን የያሬዳውያን ቃል፣ (ኤተር ፪፡፫)።

ዲቦራ

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ እስራኤልን የፈረደች እና ባርቅን ከነዓናውያን እንዲቃወም ያበረታታ ችው ነቢይቷ (መሳ. ፬)። የዲቦራና የባርቅ መዝ ሙሮች የእስራኤልን ከምርኮ ነጻ መሆንን ያከብ ራል (መሳ. ፭)።

ዲያቆን፣ ደግምም፣ አሮናዊ ክህነት ተመልከቱ

በሐዋሪያው ጳውሎስ ዘመን በቤተክርስቲያኗ ውስጥ የነበረ ጥሪ (ፊልጵ. ፩፡፩፣ ፩ ጢሞ. ፫፡፰–፲፫) እናም በአሮናዊ ክህነት ውስጥ ያለ ሀላፊነት (ት. እና ቃ. ፭፡፴፰፣ ፶፯–፶፱፣ ፹፬፡፴፣ ፹፣ ፹፲፩፣ ፹፯፡፹፭)።

ዲያብሎስ፣ ደግምም መንፈስ—ክፉ መንፈሶች፣ ሲያል፣ አጥቢያ ኮከብ፣ አፍራሽ፣ የክርስቶስ ተቃዋሚ፣ የጥፋት ልጆች ተመልከቱ

ሰይጣን ዲያብሎስ ጽድቅንና የእግዚአብሔርን ፍላጎት ለሚፈልጉት ጠላት ነው። እርሱም የእግዚ አብሔር የመንፈስ ልጅ እናም በአንድ ጊዜም በእ ግዚአብሔር ፊት ስልጣን የነበረው መልአክ ነበር። ነገር ግን፣ በቅድመ ምድራዊ ህይወት አመጸና የአ ብን አንድ ሶስተኛ የመንፈስ ልጆች ከእርሱ ጋር እን ዲያምጹ አሳመናቸው (ኢሳ. ፲፬፡፲፪፣ ፪ ኔፊ ፪፡፲፯) (ት. እና ቃ. ፳፱፡፴፯፣ ሙሴ ፬፡፩–፬፣ አብር. ፫፡፳፯–፳፰)። ከሰማይ ተወረወሩ፣ ስጋዊ ሰውነት የማግኘትና ምድራዊ ህይወት ለማግኘት እድል አል ተሰጣቸውም፣ እናም ለዘለአለምም ተኮነኑ። ዲያ ብሎስ ከሰማይ ከተወረወረ ጊዜ በኋላ፣ የሰውን ዘር ሁሉ እንደ እርሱ መከረኛ እንዲሆኑ ሁሉንም ወን ዶችና ሴቶች ለማታለል እና ከእግዚአብሔር ስራ ውጪ መርቶ ለመውሰድ በየጊዜው ሞክሯል(ራዕ. ፲፪፡፱፣ ፪ ኔፊ ፪፡፳፯፣ ፱፡፳–፴)።

ኢየሱስ ዲያብሎስን ገሠጸው፣ ማቴ. ፲፯፡፲፰። ለሰይጣንና ለመላእክቱ የዘላለም እሳት ተዘጋጅ ቷል፣ ማቴ. ፳፭፡፵፩። ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል፣ ያዕ. ፬፡፯።

ክፉዎች ወደ ዲያብሎስ ምርኮ ይወርዳሉ፣ ፮ ኔፊ ፲፬፡፯። ዲያብሎስ የሀሰቶች ሁሉ አባት ነው፣ ፪ ኔፊ ፪፡፲፰ (ሙሴ ፬፡፬)። ዲያብሎስ የሰውን ዘር ሁሉ እንደ እርሱ መከረኛ እንዲሆኑ ይፈልጋል፣ ፪ ኔፊ ፪፡፳፯። ስጋ የማይነሳ ቢሆን ኖሮ መንፈሳችን ለዘ ለዓለም ለዲያብሎስ ተገዢዎች ይሆኑ ነበር፣ ፪ ኔፊ ፱፡፴–፴፱። ዲያብሎስ ይቆጣል፣ ያረጋጋል፣ እናም ያሞግሳል፣ ፪ ኔፊ ፳፰፡፳–፳፫። ክፉ የሆነው ከዲ ያብሎስ ይመጣል፣ ኦምኒ ፩፡፳፭ (አልማ ፭፡፴፣ ሞሮኒ ፯፡፲፪፣ ፲፯)። በመካከላችሁ ፀብ እንዳይነሳ፣ እና በእርኩስ መንፈስ ከመታዘዝ ተጠንቀቁ፣ ሞዛያ ፪፡፴፪። የመልካሙ እረኛ በጎች ካልሆናችሁ፣ ዲያ ብሎስ እረኛችሁ ነው፣ አልማ ፭፡፴፯–፴፱። ዲያ ብሎስ ልጆቹን አይደግፍም፣ አልማ ፴፡፳። በዲ ያብልስ ፈተናዎች እንዳትወሰዱ ሁልጊዜም ጸልዩ፣ አልማ ፴፬፡፴፱ (፫ ኔፊ ፲፳፡፲፣ ፲፳)። የዲያብሎስ ኃይለኛ ንፋሱ፣ አዎን፣ በእናንተን ላይ ኃይል እንዳ ይኖረው ዘንድ በአዳኝ መሰረታችሁን ገንቡ አስታ ውሱ፣ ሔለ. ፭፡፲፪። ዲያብሎስ የኃጢያቶች ሁሉ ጸሀፊ ነው፣ ሔለ. ፮፡፳፯–፴፩።

ዲያብሎስ አጭበርባሪ እቅድ ለማቀድ ፈልጓል፣ ት. እና ቃ. ፲፡፲፪። ሰይጣን የሰዎችን ልጆች ይፈ ትን ዘንድ ግድ ነው፣ ካልሆነ በራሳቸው ለራሳቸው መምረጥ አይችሉም፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፴፱። ዲያ ብሎስ አዳምን ፈተነው፣ እናም የተከለከለውን ፍሬ በላ እናም ትዛዙን ተላለፈ፣ በዚህም ለፈተና እራሱን አሳልፎ በመስጠቱ ምክንያት በሰይጣን ፈቃድ ተገዢ ሆነ፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፴። የጥፋት ልጆች ከዲያብሎስና ከመላእክቱ ጋር ለዘለአለም ይነግሳሉ፣ ት. እና ቃ. ፫፲፯፡፴፪–፴፫፣ ፴፰። ዲያ ብሎስ ለአንድ ሺህ አመት ይታሰራል፣ ት. እና ቃ. ፹፰፡፹፣ (ራዕ. ፳፡፪)። ክፉው ብርሀንና እውነትን ወሰደ፣ ት. እና ቃ. ፹፫፡፴፱።

ሰይጣን ሁለተኛ ሁኔታውን አልጠበቀም፣ አብር. ፫፡፳፰።

የዲያብሎስ ቤተክርስቲያን፣ በምድር ውስጥ ንጹህንና ፍጹም የሆነውን ወንጌል የሚለውጡና ከእግዚአብሔር ጥቦ ጋር የሚዋጉ ክፉ እና አለማዊ የሆኑ ድርጅቶች።

ዲያብሎስ ታላቋና የርኩሰቱን ቤተክርስቲያን መሰረተ፣ ፤ ኔፊ ፲፮፡፲ (፤ ኔፊ ፲፬፡፱)። ሁለት ቤተክርስቲያናት ብቻ አሉ፤ አንዷ የእግዚአብሔር በግ ቤተክርስቲያን ናት፣ ሌላዋም የዲያብሎስ ቤተ ክርስቲያን ናት፣ ፤ ኔፊ ፲፬፡፲ (አልማ ፭፡፴፱)።

የዲያብሎስ ቤተክርስቲያን ካልሆነ በስተ ቀር ከማንም ቤተክርስቲያን ጋር አትከራከሩ፣ ት. እና ቃ. ፲፰፡፭ ታላቋና የርኩሰት ቤተክርስ ቲያን ትጣላለች፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፳፭።

ዳርዮስ። *ደግምም ባቢሎን ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ ከብልጣሶር ሞት በኋላ በባቢሎን የሚዶናውያን ንጉስ የነበረው (ዳን. ፭፡፴፩፤ ፮፡፱፣ ፳፡፩፣ ፳፡፩–፳፡፣ ፳፡፩፣ ፲፩፡፩)።

ዳን። *ደግምም እስራኤል፣ ያዕቆብ፣ የይስሐቅ ልጅ ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ የያዕቆብና የራሔል ገረድ የባላ ልጅ (ዘፍጥ. ፴፡፭–፮)።

የዳን ጎሳ፣ ያዕቆብ ለዳን የሰጠውን በረከት ለማየት፣ ዘፍጥ. ፵፱፡፲፮–፲፰ ተመልከቱ። ሙሴ ለዳን ጎሳዎች የሰጠውን በረከቶች ለማየት፣ ዘዳግ. ፴፫፡፳፭ ተመልከቱ። በከነዓን ከሰፈሩ በኋላ፣ የዳን ጎሳዎች ትንሽ ግን በጣም የለማች መሬት ተሰጣቸው (ኢያ. ፲፱፡፵–፵፰)። ከአሞራውያን (መሳ. ፩፡፴፬) እና ከፍልስጤማውያን (መሳ. ፲፫፡፪፣ ፳፭፡፣ ፲፳፡፩) ይህን ለመከላከል ታላቅ ችግር ነበራቸው። በዚህም ምክንያት፣ ዳናውያን ወደ ሰሜን ፍልስጤም (መሳ. ፲፰)፣ በሌሳ አካባቢ ሄዱ፤ ከተማውንም ዳን ብለው ጠሩት። ይህም “ከዳን ወደ ቤርሳቤህ” የተዘረጋ በደ ንብ የታወቀ የፍልስጤም የሰሜን ከተማ ወሰን ነው።

ዳንኤል

በብሉይ ኪዳን በትንቢተ ዳንኤል ውስጥ ዋናው ሰው። የእግዚአብሔር ነቢይና የታላቅ እምነት ሰው።

ስለወላጆቹ ምንም አይታወቅም፣ ነገር ግን የን ጉሶች ትውልድ የሆነ ይመስላል (ዳን. ፩፡፫)። ወደ ባቢሎን በምርኮ ተወስዶ ነበር፣ በዚያም የብልጣሶር ስም ተሰጠው (ዳን. ፩፡፮–፯)። ዳንኤል እና ሌሎች ሶስት ምርኮኛዎች የንጉሱን ምግብ በጽድቅ ምክን ያት አንበላም አሉ (ዳን. ፩፡፰–፲፮)።

ዳንኤል ህልሞችን ለመተርጎም በነበረው ሀይል ምክንያት በናቡከደነፆር እና በዳርዮስ ተወዳጅ ሆነ (ዳን. ፪፣ ፱፣ ፮)። በግድግዳ ላይ የነበረውን የእጅ ጽሁፍንም አንብቦ ተረጎመ (ዳን. ፭)። ጠላቶቹ በእ ርሱ ላይ አሴሩበት፣ እና ወደ አምበሶች ጉድጓድ ተጣለ፣ ነገር ግን ጌታ ህይወቱን አዳነ (ዳን. ፮)።

ትንቢተ ዳንኤል፣ መፅሐፉ ሁለት ክፍሎች አሉት፥ ምዕራፍ ፩–፮ ስለዳንኤልና ስለሶስቱ ጓደ ኞቹ ታሪክ ናቸው፣ ምዕራፍ ፯–፲፪ ዳንኤል ያያ ቸው ነቢያዊ ራዕዮች ናቸው። መፅሐፉ ለእግዚአብ ሔር እውነተኛ የመሆንን አስፈላጊነት ያስተምራል እናም ጌታ ታማኝን እንደሚባርክ በምሳሌ ያሳያል።

መፅሐፉ ከሰጣቸው ታላቁ የንጉስ ናቡከደነፆር ህልም ትርጉም ነው። በህልሙ ውስጥ የእግዚአ ብሔር መንግስት በመጨረሻው ቀናት ከተራራው እንደ ተፈነቀለ ድንጋይ ጋር ይመሳሰላል። ድንጋዩም ምድርን በሙሉ እስከሚሸፍን ድረስ ይንከባለላል (ዳን. ፪፣ ደግምም ት. እና ቃ. ፰፡፭፣ ፪ ተመልከቱ)።

ዳኛ፣ ፍርድ። *ደግምም መኮነን፣ ኩነኔ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ—ዳኛ፣ ፍርድ፣ የመጨረሻው ተመልከቱ*

ጸባይን በወንጌል መሰረታዊ መርሆች መመዘን፣ መወሰን፣ ጥሩን ከመጥፎ መለየት።

ሙሴ በሕዝቡ ሊፈርድ ተቀመጠ፣ ዘፀአ. ፲፰፡፲፣ ፲፫። ለባልንጀራህ በእውነት ፍረድ፣ ዘሌዋ. ፲፱፡፲፭።

እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ፣ ማቴ. ፯፡፩ (ጆ.ስት.፣ ማቴ. ፯፡፩–፪፣ ሉቃ. ፮፡፴፯፣ ፫ ኔፊ ፲፬፡፩)። ኃጢአት ያደረጉ ሁሉ በሕግ ይፈረድባ ቸዋል፣ ሮሜ ፪፡፲፪። ቅዱሳን በዓለም ላይ ይፈር ዳሉ፣ ፩ ቆሮ. ፮፡፪–፫።

የዘለዓለማዊው እግዚአብሔር ልጅ በዓለም ተፈ ረደበት፣ ፤ ኔፊ ፲፩፡፴፪። የበጉን አስራ ሁለት ሐዋ ርያት የእስራኤል አስራ ሁለቱን ነገዶች ይፈርዳሉ፣ ፤ ኔፊ ፲፪፡፱፣ ፱ (ት. እና ቃ. ፳፱፡፲፪)። ሞት፣ ሲኦል፣ ዲያብሎስና በእነርሱም የተያዙት ሁሉ ይፈረድባ ቸዋል፣ ፪ ኔፊ ፳፰፡፳፣ ፳፩ (፤ ኔፊ ፲፭፡፴፫)። አንድ ሰው ካላችሁ ሀብት እንድታካፍሉት የሚጠይቃ ችሁን ከፈረዳችሁበት፣ ሀብታችሁን በመያዛችሁ ኩነኔያችሁም ምን ያህል ትክክል ይሆናል፣ ሞዛያ ፬፡፳፪። ሰዎች እንደስራቸው ይፈረድባቸዋል፣ አልማ ፵፭፡፫። በትክክል ፍረድ፣ በድጋሚም ፍትህ ይመለስልሃል፣ አልማ ፵፭፡፲፡ ከሚፃፉት መጽ ሐፍት ይህ ህዝብ ይፈረድበታል፣ ፫ ኔፊ ፳፯፡፳፫–፳፯ (ራዕ. ፳፡፲፪)። በዚህች ምድር ኢየሱስ በመሪ ጣቸው በአስራ ሁለቱ የሕዝቦች ቅሪት ይፈረድባ ቸዋል፣ ሞር. ፫፡፲፳–፳፡ ሞርሞን ጥሩን ከመጥፎ የሚፈረድበትን መንገድ ገለጸ፣ ሞሮኒ ፯፡፲፱–፲፳፡

ወደ መልካም በሚመራው መንፈስ ላይ እምነት ህን አድርግ፣ ት. እና ቃ. ፲፩፡፲፪። በልባችሁም እን ዲህ ማለት ይገባችኋል—በእኔ እና በአንተ መካከል እግዚአብሔር ይፍረድ፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፲፩። የጌታ ቤተክርስቲያን አገሮችን ተፈርዳለች፣ ት. እና ቃ. ፳፱፡፴፯–፴፳፡ እንደሰዎች በሥጋ እንዲፈረድባ ቸው ዘንድ ወልድ በወኒኒ ውስጥ የነበሩት የሰዎች ነፍሶች ነበኛቸው፣ ት. እና ቃ. ፹፯፡፹፫ (፤ ጴጥ. ፬፡፮)። ኤጲስ ቆጶስ ዳኛ ይሆናል፣ ት. እና ቃ. ፲፯፡፹፪–፹፬። ጌታ ሁሉንም ሰዎች በስራዎቻቸው

መሰረት፣ በልቦቻቸው ፍላጎት መሰረት ይፈርድባ ቸዋል፣ ት. እና ቃ. ፤፴፯፤ ፴።

ዳዊት። ደግምም መዝሙረ ዳዊት፣ ቤርሳቤህ ተመልከቱ

በብሉይ ኪዳን ውስጥ የጥንት እስራኤል ንጉስ።

ዳዊት የይሁዳ ጎሳ አባል የሆነው የእሴይ ልጅ ነበር። አንበሳ፣ ድብ፣ እና ፍልስጥኤማዊ የጌት ሰው ጎልያድን የገደለ ብርቱ ወጣት ነበር (፩ ሳሙ. ፲፯)። ዳዊት የእስራኤል ንጉስ እንዲሆን ተመርጦ ተቀባ። እንደ ሳኦል፣ በጎልማሳ ህይወቱ በክፉ ጥፋት ወን ጀለኛ ነበር፣ ነገር ግን ሳኦል እንዳላደረገው እርሱ ለእውነተኛ ጸጸት ችሎታ ነበረው። ስለዚህ ከኦርዮ ግድያ በስተቀር ይቅርታን ለማግኘት ችሎ ነበር (ት. እና ቃ. ፲፴፪፣ ፴፱)። ህይወት በአራት ክፍሎች ለመከፋፈል ይችላሉ፥ (፩) እረኛ በነበረበት በቤተ ልሔም (፩ ሳሙ. ፲፮–፲፯)፣ (፪) በንጉስ ሳኦል ቤተ መንግስት (፩ ሳሙ. ፲፰፡፩–፲፱፡፲፰)፣ (፫) እንደ ስደተኛ (፩ ሳሙ. ፲፱፡፲–፴፩፡፲፫)፣ ፪ ሳሙ. ፩)፣ (፬) በኬብሮን ውስጥ እንደ ይሁዳ ንጉስ (፪ ሳሙ. ፪–፬)፣ እና በጎላም እንደ ሙሉ እስራኤል ንጉስ (፪ ሳሙ. ፭–፳፬፣ ፩ ነገሥ. ፩፡፩–፪፡፲፩)።

ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር በዝሙት የፈጸመው ኃጢ ያት የህይወቱን የመጨረሻ ሀያ አመትን ባጠፉበት መጥፎ እድሎች ተከታትለዋል። በንግስናው ዘመን ሀገሩ በሙሉ በልፅገው ነበር፣ ነገር ግን ዳዊት በኃ ጢያቶቹ ውጤቶች ምክንያት ተሰቃየ። ብዙ የቤተ ሰብ ጸብ ነበሩ፣ በዚህም አቤሴሎምና አዶንያስ በግ ልጽ አመጹ። እነዚህ ችግሮች ነቢዩ ናታን በዳዊት ላይ በኃጢያቶቹ ምክንያት ያስታወቃቸው የተሟ ሉበት ነበሩ (፪ ሳሙ. ፲፪፡፲–፲፫)።

እነዚህ ሀይለኛ ጥፋቶች ቢኖሩም፣ የዳዊት ግዛት በእስራኤላውያን ታሪክ ሁሉ በጣም አስደናቂ የነበረ ነው፣ ምክንያቱም (፩) ጎሳዎችን በአንድ ሀገር አስ ተባበራቸው፣ (፪) ሀገሩን ያለብጥበጣ ሀላፊነት ያዘ፣ (፫) መንግስትን በእውነተኛው ሀይማኖት ላይ በመ መስረት የእግዚአብሔርን ፍላጎት የእስራኤል ህግ አደረገ። ለዚህ ምክንያት፣ በጎላም የዳዊት ግዛት የሀገሩ ወርቃማ ዘመን እና መሲህ በሚመጣበት ጊዜ እንደሚሆነው ግርማዊ እድሜ አይነት ምሳሌ እንደ ሆነ ታስቦበታል (ኢሳ. ፲፯፡፩፤ ኤር. ፳፫፡፭፤ ሕዝ. ፴፯፡፳፬–፳፰)።

የዳዊት ህይወት ሁሉም ሰዎች እስከ መጨረሻ በጻድቅ ለመፅናት አስፈላጊነትን የሚያሳይ ነበር። እንደ ወጣትነቱ፣ እርሱ "እግዚአብሔር እንደ ልቡ የሆነ ሰው" ነው ተብሎ ነበር (፩ ሳሙ. ፲፫፡፲፬)፤ እንደ ጎላምሳም፣ በመንፈስ ተናገረ እናም ብዙ ራዕያትም ነበሩት። ነገር ግን ለእግዚአብሔር ትእ ዛዛት ታዛዥ ባለመሆኑ ከባድ የሆነ የቅጣት ክፍያ ነበረበት (ት. እና ቃ. ፲፴፪፡፴፱)።

ዳግመኛ መወለድን፣ ከእግዚአብሔር መወለድ። ደግምም መቀየር፣ የተቀየረ፤ መወለድ፤ የእግዚአብሔር ወንድ እና ሴት ልጆች፤ የክርስቶስ ልጆች፤ ጥምቀት፣ መጥመቅ፤ ፍጥረታዊ ሰው ተመልከቱ

የጌታ መንፈስ በሰው ልብ ውስጥ ታላቅ ለውጥ በማምጣት ምንም ክፉ ለማድረግ ፍላጎት ሳይሆን፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ነገሮች ለማድረግ ፍላጎት እንዲኖረው ማድረግ።

በውስጣችሁ አዲስ መንፈስ እስገባለሁ፣ ሕዝ. ፲፩፡፲፱ (ሕዝ. ፲፰፡፴፩፣ ፴፯፡፳፮)።

በክርስቶስ ስም የሚያምኑት እነርሱም ከእግዚአ ብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም አልተወለዱም፣ ዮሐ. ፩፡፲፪–፲፫። ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይች ልም፣ ዮሐ. ፫፡፫–፯። በእግዚአብሔር ቃል እንደ ገና ለመወለድ እንችላለን፣ ፩ ጴጥ. ፩፡፫–፳፫። በእ ግዚአብሔር የተወለደም በኃጢያት አይቀጥልም፣ ፩.ዮ.ት.፣ ፩ ዮሐ. ፫፡፱። ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋልና፣ ፩ ዮሐ. ፭፡፬።

በክርስቶስ የተወለዱ ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ይገባሉ፣ ሞዛያ ፫፡፲፱፣ ፭፡፪–፯። ሁሉም ሰዎች እንደገና መወለድ፣ አዎን በእግዚአብሔር መወ ለድ አለባቸው፣ ሞዛያ ፳፯፡፳፭–፳፱ (አልማ ፭፡፶፱)። በመንፈስ በእግዚአብሔር የተወለዳችሁ ናችሁ፣ አልማ ፭፡፲፪–፲፱። በድጋሚ ካልተወለ ዳችሁ መንግስተ ሰማያትን መውረስ አትችሉም፣ አልማ ፯፡፲፩።

ቃሌን የሚያምኑ ሁሉ...፣ ከእኔም ይወለዳሉ፣ እንዲሁም ከውሃ እና ከመንፈስ፣ ት. እና ቃ. ፭፡፲፯።

ወደ መንግስተ ሰማያት በውሃ፣ በመንፈስ በድ ጋሚ መወለድ አለብህ፣ ሙሴ ፮፡፶፱።

ድምፅ። ደግምም ራዕይ ተመልከቱ

በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ እንደሚጠቀሙ በት፣ አንዳንዴ በጌታ ወይም በመልእክተኞቹ በድ ምፅ የሚሰጥ በደንብ የሚሰማ መልእክት። የመንፈስ ድምፅ ደግሞም በደንብ አይሰማም እና በቀጥታ ወደ ልብ ወይም አዕምሮ የሚመጣ ሊሆንም ይችላል።

አዳም እና ሔዋን የእግዚአብሔርን የአምላ ክን ድምፅ ሰሙ፣ ዘፍጥ. ፫፡፰ (ሙሴ ፬፡፲፱)። ጌታ ለኤልያስ በትንሽ የዝምታ ድምፅ አነጋገረው፣ ፩ ነገሥ. ፲፱፡፲፩–፲፫።

ጻድቅ የመልካሙ እራኛ ድምፅን ይከተላሉ፣ ዮሐ. ፣፡፩–፲፮። ከእውነት የሆነ ሁሉ ድምፄን ይሰ ማል፣ ዮሐ. ፲፰፡፴፯።

ለመንፈስም ድምፅ ታዘዝኩ፣ ፩ ኔፊ ፬፡፯–፲፰። ድምፅ ወደእኔ መጣ፣ እንዲህም አለኝ ኢኖስ ኃጢ ያትህ ይቅር ተብሎልሃል፣ ኢኖስ ፩፡፭። ለስላሳና

ፍፁም የሆነ ድምፅ ነበር፣ እናም ነፍስንም እንኳን የሚወጋ ነበር፣ ሔለ. ፮፡፳፱–፴፫ (፲ ኔፊ ፲፩፡፲–፲፯)።

በእኔ ድምጽ ሆነ በአገልጋዮቼ ድምጽ፣ ያም አንድ ነው፣ ት. እና ቃ. ፩፡፴፯። በመንፈስ ቅዱስ ሲነሳሱ የሚናገሩት ማንኛውም ነገር ቅዱሳት መጻህፍት ይሆናሉ፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፪–፱። ድምጼን የሚያከብር ነፍስ ሁሉ ፊቴን ያያል እና እኔ እንደ ሆንኩም ያውቃል፣ ት. እና ቃ. ፶፫፡፩።

ድምፅ መስጠት። *የጋራ ስምምነት ተመልከቱ*

ድቅድቅ ጨለማ። *መንፈሳዊ ሞት፣ ሲያል፣ የጥፋት ልጆች፣ ዲያብሎስ ተመልከቱ*

ድንኳን። *ታቦት ተመልከቱ*

ድንጋይ። *አለት ተመልከቱ*

ድንግል። *ደማሞም ማርያም፣ የኢየሱስ እናት ተመልከቱ*

የፍትወተ ስጋ ግንኙነት ፈፅመው የማያውቁ ለማ ግባት እድሜ የደረሰ ወንድ ወይም የደረሰች ሴት። በቅዱሳት መጻህፍት ውስጥ፣ ድንግል ስነምግባር ጥሩ የሆነን ሰው የሚወክል ነው (ራዕ. ፲፬፡፬)።

ድንግል ትፀንሳለች፥ ወንድ ልጅም ትወልዳ ለች፣ ኢሳ. ፯፡፲፬ (ማቴ. ፩፡፳፫፣ ፪ ኔፊ ፲፯፡፲፬)።

መንግስተ ሰማይ እንደ አስር ድንግሎች ተመሳ ስሏል፣ ማቴ. ፳፭፡፩–፲፫።

በናዝሬትም ከተማ የእግዚአብሔር ልጅ እናት የሆነችን አንዲት ድንግል ተመለከትኩ፣ ፩ ኔፊ ፲፩፡፲፣–፲፰። ማርያም የተከበረች እንዲሁም የተ መረጠች ዕቃ ናት፣ **አልማ** ፯፡፲።

ድንግልነት። *ንጹህነት ተመልከቱ*

ድንግሏ ማርያም። *ማርያም፣ የኢየሱስ እናት ተመልከቱ*

ጄረም

በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ፣ የኢኖስ ልጅ እና የሌሂ የልጅ ልጅ ልጅ። ከ፬፻፳፭–፲፻፳፭ ም.ዓ. ድረስ ለ፳ አመት የኔፋውያንን መዝገብ ጠበቀ (ኢኖስ ፩፡፳፭፤ ጄረም ፩፡፲፣)። በታሪካዊ መዝገቡ ላይ ብዙ ላለመጻፍ ውሳኔ ያደረገ ታማኝ ሰው ነበር (ጄረም ፩፡፪)።

መፅሐፈ ጄረም፣ በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ በዚህ መፅሐፍ ውስጥ አስራ አምስት ቁጥሮች ብቻ ነው ያሉት። ጄረም ኔፋውያን በሙሴ ህግ ለመኖር እንደቀጠሉ እናም የክርስቶስ መምጣትን በጉጉት እንደሚጠብቁ መዘገበ። በእምነት ኃይለኛ ሰዎች በሆኑ ንጉሶች ይመሩም ነበር። ነቢያቸውን፣ ካህና ታቸውን፣ እና መምሁራቸውን ሲያዳምጡ በለጸጉ።

ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ። *ስሚዝ፣ ጆሴፍ ዳግማዊ ተመልከቱ*

ጆሮ። *ደማሞም ማዳመጥ ተመልከቱ*

በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ፣ ጆሮ እንደ ሰው የማዳመጥ ወይም የእግዚአብሔር ነገሮችን የማስ ተዋል ችሎታ ምልክት የሚጠቀሙበት ነው።

ጆሮ አላቸው አይሰሙም፣ መዝ. ፻፲፭፡፮። ጌታ እንድሰማ ዘንድ ጆሮዬን ያነቃቃል፣ ኢሳ. ፶፡፬–፭ (፪ ኔፊ ፯፡፬–፭)።

የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ፣ ማቴ. ፲፩፡፲፭። ጆሮአቸውም ደንቁሮአል፣ ማቴ. ፲፫፡፲፭ (ሙሴ ፮፡፳፯)። ዓይን ያላየችው ጆሮም ያልሰማው እግ ዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው፣ ፩ ቆሮ. ፪፡፱ (ት. እና ቃ. ፳፯፡፲)።

ዲያብሎስ በጆሮአቸው አሾከሾከ፣ ፪ ኔፊ ፳፭፡፳፡፳፪። ትሰሙ ዘንድ ጆሮአችሁን ክፈቱ፣ ሞዛያ ፪፡፱ (፲ ኔፊ ፲፩፡፳)። ለብዙ ጊዜ ተጠርቻለሁ፣ እናም አላዳመጥኩም፣ **አልማ** ፲፡፮። ቃሌን አድ ምጥ፣ **አልማ** ፴፮፡፩ (አልማ ፴፫፡፩፣ ት. እና ቃ. ፶፫፡፩)።

የማይሰማ ጆሮ አይኖርም፣ ት. እና ቃ. ፩፡፪። ጆሮዎቹ የሚከፈቱት በትሁትነትና በጸሎት በኩል ነው፣ ት. እና ቃ. ፲፴፮፡፴፪።

ገሊላ

በጥንት እና በዚህም ዘመን፣ በዮርዳኖስ ወን ዝና በገሊላ ባህር በስተምዕራብ የሚገኝ የእስራኤል ሰሜናዊ አውራጃ። ገሊላ ዘጠና ሰባት ኪሎ ሜትር ረጅምና አርባ ስምንት ኪሎ ሜትር ስፋት ያለው ነው። በጥንት ጊዜ፣ ከሁሉም በላይ ጥሩ የሆኑ ምድ ርንና ከእስራኤል ከተማዎች በላይ በጣም ስራ የበዙ ባቸው ከተማዎችን የያዘ ነው። ወደ ደማስቆ፣ ወደ ግብፅ፣ እና ወደ ምስራቅ እስራኤል የሚመሩ አውራ መንገዶች በገሊላ በኩል ያልፋሉ። ጥሩም የአየር ጠባዩ እና የለማ አፈሩ ብዙ ወይራ፣ ስንዴ፣ ገብ ስና፣ ወይኖች ያሳድጋሉ። በገሊላ ባህር የሚገኙት የአሳ ማርቢያዎች ብዙ ወደ ውጪ ሀገር የሚሸጡ ትን ያስገኛሉ እናም የታላቅ ሀብት ምንጭ ነበሩ። ጌታ ብዙ ጊዜውን በገሊላ ውስጥ አሳለፈ።

በገሊላ ታላቅ ብርሀን ይበራል፣ ኢሳ. ፱፡፩–፲ (፪ ኔፊ ፲፱፡፩–፲)።

ኢየሱስም እያስተማረ እየሰበከ እየፈወሰ በገሊላ ሁሉ ይዞር ነበር፣ ማቴ. ፬፡፳፫። ኢየሱስ ከሞት ከተነሳ በኋላ፣ በገሊላ ታየ፣ ማር. ፲፮፡፳፰ (ዮሐ. ፳፩፡፩–፲፬)። ኢየሱስም በገሊላ ሁሉ ዝና ወጣ፣ ሉቃ. ፬፡፲፬። ኢየሱስ ይህን የምልክቶች መጀመ ሪያ በገሊላ ቃና አደረገ፣ ዮሐ. ፪፡፲፩።

የገሊላ ባህር፣ የገሊላ ባህር በሰሜን እስራኤል

የሚገኝ ነው። ይህም በብሉይ ኪዳን ውስጥ ኪኔሬት ባሕር እና በአዲስ ኪዳን ውስጥ የጌንሴሬጥ ሀይቅ ወይም ጥብርያዶስ ተብሎ ይጠራል። ኢየሱስ ብዙ ስብከቱን በእዚያ አደረገ (ማቴ. ፲፫፡፪)። ባህሩ ሸክኒት አይነት ቅርጽ የነበረው፣ ፷ ኪሎ ሜትር ረጅም እና ሰፊ በሆነበት ቦታ ላይ ፲፪ ኪሎ ሜትር የሰፋ ነበር። ከባህር አማካይ ጥልቀት ከ፪፻፲፯ ሜትር በታች ይገኛል፣ ይህም በአካባቢው የሚገኘውን አየር በጣም የሞቀ ያደርገዋል። ቀዝቃዛ አየሩ ከኩረ ብታው ወደታች ወርዶ ከውሀው በላይ ከሚገኘው ሙቅ ውሀ ጋር በመገናኘት የድንገት ሀይለኛ ዝናብ ይጀምራል (ሉቃ. ፰፡፳፪–፳፭)።

ገማልኤል። *ደግሞም ፈሪሳዊያን ተመልከቱ*

በአዲስ ኪዳን ውስጥ የአይሁዳ ህግን የሚያ ውቅ እና የሚያስተምር ታዋቂ ፈሪሳዊ። ሐዋሪያ ጳውሎስ ከእርሱ ተማሪዎች አንዱ ነበር (የሐዋ. ፳፪፡፣፫)። በሳንሀድርን ውስጥ ብዙ ተፅዕኖ የነበረው ነበር (የሐዋ. ፭፡፴፬–፴፱)።

ገሞራ። *ደግሞም ሰዶም ተመልከቱ*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ በጌታ የጠፋ ክፍይ ከተማ (ዘፍጥ. ፲፱፡፲፪–፳፱)።

ገር፣ ገርነት። *ደግሞም ትሁት፣ ትሕትና፣ ትዕግስት፤ የተሰበረ ልብ ተመልከቱ*

እግዚአብሔርን የሚፈራ፣ ጻድቅ፣ ትሁት፣ ለመ ማር ፈቃደኛ፣ እና በስቃይ ትእግስተኛ የሆነ። ትሁ ቶች የወንጌል ትምህርቶችን ለመከተል ፈቃደኞች ናቸው።

ሙሴም እጅግ ትሑት ሰው ነበረ፣ ዘኁል. ፲፪፡፣፫። ገሮች ግን ምድርን ይወርሳሉ፣ መዝ. ፴፯፡፲፩ (ማቴ. ፭፡፭፣ ፣ ፣ ኔፊ ፲፪፡፭፣ ት. እና ቃ. ፹፯፡፲፣፲፯)። እናንተ የምድር ትሑታን ሁሉ፥ እግዚ አብሔርን ፈልጉ፤ ጽድቅንም ፈልጉ፥ ትሕትናንም ፈልጉ፣ ሶፎ. ፪፡፣ (፩ ጢሞ. ፮፡፣፲፩)።

ከእኔም ተማሩ፥ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና፣ ማቴ. ፲፩፡፳፱። የዋህነት የመንፈስ ፍሬ ነው፣ ገላ. ፭፡፳፪–፳፫። የጌታም ባሪያ ለሰው ሁሉ ገር ለማስ ተማርም የሚበቃ በትዕግሥትም የሚጸና የሚቃወ ሙትን በየዋህነት የሚያስተምር መሆን አለበት፣ ፪ ጢሞ. ፪፡፳፬–፳፭። በእግዚአብሔር ፊት ዋጋው እጅግ የከበረ የዋህና ዝግተኛ መንፈስ ያለው ነው፣ ፩ ጴጥ. ፣፡፣። ተፈጥሮአዊው ሰውነትን ቀይር እናም የዋህ ይሁን፣ ሞዛያ ፣፡፣ (አልማ ፲፣፡፳፯–፳፰)። እግ ዚአብሔር ሄላማንን ሰዎች የዋህ፣ እንዲሆኑ እንዲ ያስተምራቸው አዘዘ፣ አልማ ፴፯፡፴፣። የጌታ ፀጋ ለየዋሆች በቂ ነው፣ ኤተር ፲፪፡፳፯። የዋህ በመሆ ናችሁ በክርስቶስ እምነት አላችሁ፣ ሞሮኒ ፯፡፴፱። ማንም በልቡ የሚራራ እናም የዋህ ካልሆነ በጌታ ፊት ተቀባይነት አይኖረውም፣ ሞሮኒ ፯፡፴፭። የኃ ጢያት ስርየት የዋህነትን በመንፈስ ቅዱስ መጎብኘ ትን ያመጣል፣ ሞሮኒ ፰፡፳፯።

በመንፈሴ በትህትና ተጓዝ፣ ት. እና ቃ. ፣፡፳፡፳፣። ቤትህን በትህትና ግዛ፣ ት. እና ቃ. ፴፭፡፱። የክህ ነት ሀይል እና ተፅዕኖ ሊጠበቅ የሚቻለው በደግ ነት፣ እና በትሁትነት ነው፣ ት. እና ቃ. ፻፳፭፡፴፭።

ገብርኤል። *ደግሞም መላእክት፤ ማርያም፣ የኢየሱስ እናት፤ ኖኅ፣ የመፅሐፍ ቅዱስ የአባቶች አለቃ ተመልከቱ*

ወደ ዳንኤል (ዳን. ፰፡፣፲፯፣ ፱፡፳፭)፣ ዘካሪያስ (ሉቃ. ፩፡፣፲፩–፣፲፱፣ ት. እና ቃ. ፳፯፡፣፯)፣ ማሪ ያም (ሉቃ. ፩፡፳፯–፴፰) እና ሌሎች (ት. እና ቃ. ፲፳፰፡፣፳፭)፣ የተላከ መልአክ። ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ ገብርኤል የብሉይ ኪዳን ነቢይ ኖህ እንደሆነ አስ መልክቷል።

ገነት። *ደግሞም ሰማይ ተመልከቱ*

ከዚህ ህይወት የሄዱ እና የሰውነት ትንሳኤን የሚ ጠብቁ ጻድቅ ነፍሳት የሚሄዱበት የመንፈስ አለም ክፍል ነው። ይህም የደስታ እና የሰላም ሁኔታ ነው።

ገነት በቅዱሣት መጻህፍት ውስጥ የመንፈሶች አለምን (ሉቃ. ፳፫፡፣፴፫) ሰለስቲያል መንግስት (፪ ቆሮ. ፲፪፡፣፬)፣ እና በአንድ ሺህ አመት ምድር የምትገኝበትን የክብር ሁኔታን (እ.አ. ፩፡፣) ለመ ጠቆም ይጠቀሙበታል።

ድል ለነፃው በእግዚአብሔር ገነት ካለው ከሕይ ወት ዛፍ እንዲበላ እሰጠዋለሁ፣ ራዕ. ፪፡፣፯።

የእግዚአብሔር ገነት የቅዱሳንን መንፈስ ማስ ረከብ አለባት፣ ፪ ኔፊ ፱፡፣፲፫። የፃድቃኖች መንፈስ፣ ገነት ተብላ ወደምትጠራው፣ የእረፍት ቦታ ይገ ባሉ፣ አልማ ፴፡፣፲–፣፲፪። ከሦስቱ በስተቀር ሁሉም የኢየሱስ ደቀመዛሙርት ወደ እግዚአብሔር ገነት ሄደዋል፣ ፬ ኔፊ ፩፡፣፲፬። በቅርብ ወደ እግዚአብሔር ገነት ለማረፍ እሄዳለሁ፣ ሞሮኒ ፣፡፴፬።

ክርስቶስ ጻድቅ መንፈሶችን በገነት ውስጥ አገለ ገለ፣ ት. እና ቃ. ፻፴፯፡፡

ገንዘብ። *ደግሞም ሀብቶች፤ ምፅዋት፣ የምፅዋት ስጦታ፤ አለማዊነት፤ አስራት፣ አስራት መክፈል ተመልከቱ*

የሚቀጥሉት ከንጉስ ጄምስ መፅሐፍ ቅዱስ ቅጅ የጆሴፍ ስሚዝ ትርጉም (ጆ.ስ.ት.) የተመረጡ ክፍሎች ናቸው። ጌታ የመጀመሪያዎቹ ቃላቶች ከተጻፉ በኋላ የተቀየሩትን ወይም የጠፉትን የመፅሐፍ ቅዱስ እውነቶች ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግም እንዲመልሳቸው አነሳስቶት ነበር። እነዚህ ደግመው የተመለሱ እውነቶች ትም ህርቶችን አብራርተዋል እና የቅዱስ መጻህፍት መረዳትን አሻሽለዋል።

ጌታ የመጀመሪያ ጸሀፊዎች የጻፉትን አንዳንድ እውነቶችን ለጆሴፍ ስለገለጠለት፣ የጆሴፍ ስሚዝ ትርጉም በአለም ውስጥ ካሉት ማናቸውም ሌሎች የመፅሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የተለየ ነው። በዚህም አስተያየት፣ ትር ጉም የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው ሰፋ ባለና ከልምድ በተለየ መንገድ ነው የሚጠቀምበት፣ ምክንያቱም የጆሴፍ ትርጉም ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላ የተተረጎመ ሳይሆን በራዕይ የመጣ ነበር።

የጆሴፍ ስሚዝ የንጉስ ጄምስ መፅሐፍ ቅዱስ ትርጉም ከተለያዩ የትምህርት እና ቃል ኪዳኖች ክፍሎች ጋር የተገናኘ ወይም በእነዚህ ውስጥ የተጠቀሰ ነው (ክፍሎች ፴፯፣ ፵፭፣ ፷፫፣ ፷፭፣ ፷፯፣ ፸፯፣ ፸፱፣ ና ፻፴፪ ተመልከቱ)። ደግሞም፣ መፅሐፈ ሙሴ እና ጆሴፍ ስሚዝ—ማቴዎስ ከጆሴፍ ስሚዝ ትርጉም የተወሰዱ ምን ባቦች ናቸው።

ለጆሴፍ ስሚዝ ትርጉም ተጨማሪ መረጃ፣ የቅዱሳት መጻህፍት መመሪያ ውስጥ "የጆሴፍ ስሚዝ ትርጉም (ጆ.ስ.ት.)"ን ተመልከቱ።

የሚቀጥሉት ምሳሌዎች ከጆሴፍ ስሚዝ ትርጉም የተመረጡ ናሙናዎችን ያሳያሉ።

ይህ በደመቀ አይነት የተጻፈው ጥቅስ ከንጉስ ጄምስ መፅሐፍ ቅዱስ ጆሴፍ ስሚዝ የተረጎመው ምንባብ ነው። ትርጉሙ ወደ መፅሐፍ ቅዱስ ጽሁፍ ቃላቶችን በዳግም ስለመለሰ፣ የአንቀጽ ቁጥሮች እናንተ ከምትጠቀሙበት ቅጂ የተለየ ይሆናል።

ይህ ማጣቀሻ በመፅሐፍ ቅዱሳችሁ ውስጥ የት ኛውን ጥቅሰት ከጆሴፍ ስሚዝ ትርጉም ጋር ለማ ነጻጸር እንደሚገባችሁ ይጠቁማል።

ጆ.ስ.ት.፣ ማቴዎስ ፤፡፣ ፮–፯፣ ፰–፱። ከማቴዎስ ፡፣ ፮፣ ፮–፯፣ ፲–፲፩ ጋር አነጻፅሩ፣ በሉቃስ ፡፣ ፪፣ ፭–፲፩ም እንደዚህ አይነት ቅያሬዎች ነበሩ

ኢየሱስ የተመራው በመንፈስ እንጂ በሰይጣን አይደ ለም።

በቅንፍ ውስጥ ያለው የጆሴፍ ስሚዝን ትርጉ ምን ከመፅሐፍ ቅዱሳችሁ ጋር ማነጻጸር የሚ ገባችሁ ጥቅስ ነው።

ይህ ጽሁፍ ጆሴ ስሚዝ እን ደተረጎመው ነው። (ጠመም ባለ የፊደል አጣጣል የተጻ ፉት በንጉስ ጄምስ ጽሁፍ ጋር የሚለያዩበትን ቃላቶች ለማሳየት ነው።)

፤ ከዚያ ወዲያ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር *ጋር ይሆን ዘንድ መንፈስ ወደ ምድረበዳ ወሰደው።*

፫ ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ወደ ቅድስት ከተማ *ተወሰደ፣ እና መንፈስ* እርሱን በመ ቅደስ ጫፍ ላይ አቆመው።

፮ *ከእዚያም በኋላ ዲያብሎስ ወደእርሱ መጣ* እና *እንዲህ አለው፣* መላእክቱን ስለ አንተ ያዝልሃል እግርህንም በድንጋይ ከቶ እንዳትሰናከል በእጃቸው ያነሡሃል ተብሎ ተጽፎአልና የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆ ንህ፣ ወደ ታች ራስህን ወርውር አለው።

፯ *ደግሞም፣ ኢየሱስ በመንፈስ ውስጥ ነበር፣* እና ይህም ወደ እጅግ ረጅም ወደ ሆነ ተራራ ወሰደው፣ የዓለምንም መንግሥታት ሁሉ ክብራቸውንም አሳየው።

፱ *እና ዲያብሎስም ወደ እርሱ እንደገና መጣ፣ እና አለው፣* ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ።

ጆ.ስ.ት.፣ ዘፍጥረት ፤፦፥፤–፤፰፡፡

ከዘፍጥረት ፤፥፤–፤፣፤፲፫ ጋር አነጻፅሩ

ይህ የመፅሐፍ ቅዱስ ጽሁፍ በጆሴፍ ስሚዝ በዳግም ተመልሶ ነበር እናም ከታላቅ ዋጋ ዕንቁ ውስጥ እንደ ተመረጠ የመፅሐፈ ሙሴ ታትሟል።

ጆ.ስ.ት.፣ ዘፍጥረት ፤፩፥፤፩–፤፣፡፡

ከዘፍጥረት ፤፲፥፤፲–፤፲፤ ጋር አነጻፅሩ

ከጎርፍ በኋላ፣ ኖህ ምድርን እንደገና እንዳይረግም ጌታን ጠየቀ።

፤፩ ኖኅም ለእግዚአብሔር መሠውያውን ሠራ፥ ከንጹሕም እንስሳ ሁሉ ከንጹሕን ወፎችም ሁሉ ወሰደ፥ በመሠውያውም ላይ መሥዋዕትን አቀረበ፤ እናም ለጌታ ምስጋና አቀረበ፣ እና በልቡ ተደሰተ።

፤፪ እና ጌታም ለኖህ ተናገረ፣ እናም ባረከው። እናም ኖህ መልካሙን መዓዛ አሸተተ፣ እና በልቡ አለ፤

፤፣ ምድርን ዳግመኛ ስለ ሰው እንዳይረግ ምም፥ የሰው ልብ አሳብ ከታናሽነቱ ጀምሮ ክፉ ነውና፤ ምድር እስካለች ድረስ፣ ደግ ሞም ከዚህ ቀድሞ እንዳደረገው ሕያዋንን ሁሉ እንደ ገና እንዳይመታም በጸሎት የጌ ታን ስም እጠራለሁ፤

ጆ.ስ.ት.፣ ዘፍጥረት ፤፩፥፤–፤፤፡፡

ከዘፍጥረት ፤፩፥፤፩–፤፩ ጋር አነጻፅሩ

ሰው የእንሰሳትንም ሆነ የሰዎችን ደም በማፍሰስ ተጠ ያቂ ነው። እግዚአብሔር ከኖህ እና ከወንድ ልጆቹ ጋር ከሔኖክ ጋር እንደገባው አይነት ቃል ኪዳን መሰረተ።

፤ ነገር ግን፣ እንደመብል የምሰጥህን ስጋዎች ሁሉ ደም በምድር ላይ ይፈሳል፣ ይህም የዚህን ህይወት ይወስዳል፣ እና ደሙን አትብላ።

፤፤ በእርግጥም፣ ለመብል፣ ህይወትህን ለማዳን ካልሆነ በስተቀር ደም አይፍሰስ፤ እና የእያንዳንዱን አራዊት ደም ከእጅህ እሻዋለሁ።

፤፣ እና የሰውን ደም የሚያፈስ ሁሉ፣ በሰው ደሙ ይፈስሳል፤ ሰው የሰውን ደም ማፍሰስ አይገባውምና።

፤፤ እያንዳንዱ የሰው ወንድም የሰውን ህይወት እንዲያድን ትእዛዝ እሰጣለሁ፣ ሰውን በመልኬ ፈጥሬአለሁና።

፤፥ እና ትእዛዝም እሰጣችኋለሁ፣ እናን ተም ብዙ፥ ተባዙ፤ በምድር ላይ ተዋለዱ፥ እርቡባትም።

፤፤ እግዚአብሔርም ለኖኅና ለልጆቹ እንዲህ ብሎ ተናገረ፣ እኔም እነሆ፣ ከአ ባታችሁ ሔኖክ ጋር ከእናንተና በኋላ ስለ ሚመጣው ዘራችሁ በሚለከት ያደረኩትን ቃል ኪዳኔን እመሰርታለሁ።

ጆ.ስ.ት.፣ ዘፍጥረት ፤፣፥፤፩–፤፩፤፡፡

ከዘፍጥረት ፤፣፥፤፣–፤፣ ጋር አነጻፅሩ

እግዚአብሔር ቀስተ ዳመና በሰማይ የሰራው ከሔኖክ እና ከኖኅ ጋር እርሱ የገባውን ቃል ኪዳን ለማስታወስ ነው። በመጨረሻዎቹ ቀናት የበኩራቱ ቤተክርስቲያን አጠቃላይ ስብሰባ ከምድር ጻድቅ ጋር ይቀናጃሉ።

፤፩፤ ቀስቲቱም በደመና ትሆናለች፤ እና ሰዎች ትእዛዛቴን ሁሉ ሲያከብሩ፣ ወደ እኔ የወሰድኳት የሔኖክ ከተማ ፅዮን እን ደገና ወደ ምድር ስትመጣ፣ እኔ ለአባታ ችሁ ሔኖክ የገባሁትን የዘላለም ቃል ኪዳን ለማስታወስ አያታለሁ።

፤፩፤ እና ይህም የዘላለም ቃል ኪዳኔ ነው፣ ትውልዶችህ እውነትን ሲያቅፉ፣ እና ወደላይ ሲመለከቱ፣ ከእዚያም ፅዮን ወደታች ትመለከታለች፣ እና ሰማያት ሁሉ በደስታ ይነቃነቃሉ፣ እና መሬትም በደስታ ትንቀጠቀጣለች፤

፤፤፣ እና የበኩራት ቤተክርስቲያን አጠ ቃላይ ስብሰባ ከሰማይ ይወርዳሉ፣ እና ምድርን የራሳቸው ያደርጓታል፣ እና መጨረሻው እስከሚመጣ ድረስ ቦታ ይኖ ራቸዋል። እና ይህም፣ ከአባታችሁ ሄኖክ ጋር የገባሁት የዘላለም ቃል ኪዳኔ ነው።

፤፤፤ ቀስቲቱም በደመና ትሆናለች፤ እና በእናንተም በእኔና በምድር ላይ በሚኖር ሥጋ ባለው በሕያው ነፍስ ሁሉ መካከል የገባሁትን ቃል ኪዳኔን እመሰርታለሁ።

፤፤፤ እግዚአብሔርም ኖኅን አለው፣ በእ ኔና በአንተ መካከል የመሰረትኩት የቃል

ኪዳን ምልክት ይህ ነው፤ ምክንያቱም ሥጋ ሁሉ በምድር ላይ ይገኛሉና።

ጆ.ስ.ት.፣ ዘፍጥረት ፲፬፡፳፫–፳፡

ከዘፍጥረት ፲፬፡፲–፳ ጋር አነጻፅሩ

መልከ ጼዴቅ አብርሐምን ባረከ። የመልከ ጼዴቅ ታላቅ አገልግሎት እና የመልከ ጼዴቅ ክህነት በረከቶች ተዘርዝረዋል።

፳፫ እና መልከ ጼዴቅ ደምዱን ከፍ አደረገ እና አብራምን ባረከው።

፳፬ አሁን መልከ ጼዴቅ ጽድቅን ያደረገ የእምነት ሰው ነበር፤ እና በልጅነት እግዚአብሔርን የፈራ፣ እና የአንበሳን አፍ የዘጋ፣ እና የእሳትን ሀይል ያጠፋ ነበር።

፳፭ በእግዚአብሔር ተቀባይ ከሆነ በኋላ፣ እግዚአብሔር ከሔኖክ ጋር በገባው ቃል ኪዳን ስርዓት መሰረት እንደ ሊቀ ካህን ተሹሞ ነበር።

፳፮ ይህም እንደ እግዚአብሔር ልጅ ስርዓት አይነት ነበር፤ ይህም ስርዓት ከእግዚአብሔር እንጂ፣ በሰው ወይም በሰው ፍላጎት፤ በአባት ወይም እናት፣ መጀመሪያ ቀናት ወይም መጨረሻ አመታት የሌለው ነበር።

፳፯ ለሰዎችም፣ በስሙ ለሚያምኑት ሁሉ፣ የተሰጠው በእራሱ ድምፅ ጥሪ፣ በእራሱ ፍላጎት በኩል ነበር።

፳፰ እያንዳንዱ በዚህ ስርዓት የሚሾመውና የሚጠራው በእምነት ተራራዎችን ለመስበር፣ ባህሮችን ለመከፋፈል፣ ውሀዎችን ለማድረቅ፣ ከመንገዳቸው ለማዞር ሀይል እንደሚኖረው እግዚአብሔር በራሱ ለሔኖክ እና ለዘሩ መሀላ ምሏልና፤

፳፱ የህዝቦችን ሰራዊቶች በግልፅ ለመቃወም፣ ምድርን ለመከፋፈል፣ እያንዳንዱን ቡድን ለመስበር፣ በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም፣ ሁሉንም ነገሮች በፍላጎቱ መሰረት፣ በትእዛዙ መሰረት ለማድረግ፣ ግዛትንና ሀይላትን በቁጥጥር ስር ለማዋል ዘንድ ሀይል እንደሚኖረው እግዚአብሔር ለሔኖክ እና ለዘሩ በራሱ መሃላ ገብቶላቸዋልና፤ እና ይህም ከአለም መሰረት በፊት በነበረው በእግዚአብሔር ልጅ ፍላጎት ነው።

፴፪ እና ሰዎች ይህ እምነት ኖሮአቸው፣ ወደዚህ የእግዚአብሔር ስርዓት በመምጣት ተሰውጠዋል እና ወደሰማይም አርገዋል።

፴፫ አሁን መልከ ጼዴቅ በዚህ ስርዓት ውስጥ ካህን ነበር፤ ስለዚህ በሳሌም ቦታ አገኘ፣ እና የሰላም ልዑል ተብሎም ተጠርቶ ነበር።

፴፬ እና ህዝቦቹ ጻድቅነትን አመጡ፣ ሰማይንም አገኙ፣ እና እግዚአብሔር ከምድር አለያይቶ በፊት የወሰዳትን፣ ለኋለኛው ቀናት ወይም ለአለም መጨረሻ የያዛትን፣ የሔኖክን ከተማ ፈለጉ፤

፴፭ እና ሰማያት እና ምድር እንደገና አብረው እንዲጠቀለሉ፣ እና የእግዚአብሔር ልጆች እንደ እሳት እንዲፈተኑ ዘንድ እንዲህም አለ፣ መሀላ ማለ።

፴፮ እና ይህ መልከ ጼዴቅ እንደዚህም ጻድቅነትን በመመስረት የሰማይ ንጉስ ተብሎ በህዝቡ ተጠርቶ ነበር፣ ወይም በሌላ ቃሎችም፣ የሰላም ንጉስ።

፴፯ እና ድምዱን ከፍ አደረገ፣ እና ሊቀ ካህን እና የእግዚአብሔር ጎተራ ጠባቂ ስለሆነም አብራምን ባረከ፤

፴፰ እርሱም ለደሀዎች አስራት እንዲቀበል እግዚአብሔር መደበው።

፴፱ ስለዚህ፣ አብራም ላላቸው ሁሉ፣ ከሚያስፈልገው በላይ እግዚአብሔር ለሰጠው ካለው ሀብቶች ሁሉ አስራት ለእርሱ ከፈለ።

፴ እና እንዲህ ሆኖ አለፈ፣ እግዚአብሔር አብራምን ባረከው፣ እና በገባው ቃል ኪዳን መሰረት፣ እና በመልከ ጼዴቅ በባረከው በረከቶች መሰረት፣ ሀብቶችን፣ ክብርን፣ እና መሬቶችን ለዘለአለም የእራሱ እንዲያደርጋቸው ሰጠው።

ጆ.ስ.ት.፣ ዘፍጥረት ፲፯፡፩–፲፪።
ከዘፍጥረት ፲፭፡፩–፮ ጋር አነጻፅሩ

አብርሐም ስለትንሳኤ ተማረ እናም የኢየሱስን ስጋዊ አገልግሎት ተመለከተ።

፩ እና አብራም አለ፣ ጌታ አምላክ ሆይ፣ ለዘለአለም ውርስ ይህን መሬት ለእኔ እን ዴት ትሰጠኛለህ?

፲ እና ጌታ እንዲህ አለ፣ ብትሞትም እንኳን፣ ይህን ለአንተ ለመስጠት አል ችልም?

፲፩ እና ከሞትክ፣ ይህን የእራስህ ልታ ደርገው ትችላለህ፣ የሰው ልጅ የሚኖርበት ቀን ይመጣልና፤ ነገር ግን ካልሞተ እን ዴት ለመኖር ይችላል? መጀመሪያ ህይ ወት መሰጠት አለበት።

፲፪ እና እንዲህ ሆኖ፣ አብራም ተመለ ከተ እና የሰው ልጅ ቀናትን አየ፣ እና ተደ ሰተ፣ እና ነፍሱም እረፍትን አገኘች፣ እና በጌታ አመነ፤ ጌታም ይህን ለእርሱ እንደ ጻድቅነት ቆጠረለት።

ጆ.ስ.ት.፣ ዘፍጥረት ፲፯፡፫–፲፪።
ከዘፍጥረት ፲፯፡፫–፲፪ ጋር አነጻፅሩ

ህዝቡ፣ ከጥምቀት በተጨማሪ፣ የወንጌል ስርዓቶችን አላከበሩም። እግዚአብሔር የግርዘት ቃል ኪዳን እና የልጆች ተጠያቂነት እድሜ ለአብርሐም ገለጸ።

፫ እና እንዲህ ሆኖ አለፈ፣ አብራምም በግምባሩ ወደቀ፤ እና የጌታን ስም ጠራ።

፬ እና እግዚአብሔርም እንዲህ ብሎ አና ገረው፣ ህዝቦቼ ከአስተያየቴ በተሳሳተው ይጓዛሉ፣ እና ለአባቶቻቸው የሰጠሁትን ስነ ስርዓቶቼንም አልጠበቁም፤

፭ እኔ ትእዛዝ የሰጠኋቸው ቅባትን፣ የቀብር ስነ ስርዓትን፣ ወይም ጥምቀትን አላከበሩም፤

፮ ነገር ግን ከትእዛዝ ዞር ብለዋል፣ እና ልጆችን ወደማጠብ፣ እና ደም መርጨ ትን በእራሳቸው ጀምረዋል፤

፯ እና የጻድቁ አቤል ደም የፈሰሰው ለጎጥያት ነው ብለዋል፤ እና በፊቴ በምን ተጠያቂ እንደሆኑም አላወቁም።

፰ ስለአንተ ግን፣ እነሆ፣ ቃል ኪዳኔን ከአንተ ጋር አደርጋለሁ፣ እና አንተም የብዙ አሕዛብ አባት ትሆናለህ።

፱ እናም ይህን ቃል ኪዳን የምገባው፣ ልጆችህ በአሕዛብ መካከል እንዲታወቁ ነው። ከዛሬም ጀምሮ እንግዲህ ስምህ አብ ራም ተብሎ አይጠራ፥ ነገር ግን ስምህ አብ ርሃም ይሆናል፤ ለብዙ አሕዛብ አባት አድ ርጌሃለሁና።

፲ እጅግም አበዛሃለሁ፥ ሕዝብም አደር ግሃለሁ፥ ነገሥታትም ከአንተ ይወጣሉ፣ እና ከዘሮችህም።

፲፩ እና የግርዘት ቃል ኪዳኔንን ከአንተ ጋር እመሰርታለሁ፣ እና ይህም በእኔና በአ ንተ መካከል፣ እና ከአንተም በኋላ ከዘርህ ጋር በትውልዳቸው ለዘላለም ኪዳን ይሆ ናል፤ ልጆችህ ስምንት አመት እስከሚ ሆናቸው ድረስ በፊቴ ተጠያቂ እንዳል ሆኑ ለዘላለም እንድታውቅ ዘንድ።

፲፪ እና ከአባቶቻችሁ ጋር ቃል የገባሁ ትን ቃል ኪዳኖቼን በሙሉ ጠብቅ፤ እና በአፌ የምሰጥህን ትእዛዛትንም ጠብቅ፣ እና ለአንተና ከአንተ በኋላ ለዘርህ አም ላክ እሆናለሁ።

ጆ.ስ.ት.፣ ዘፍጥረት ፲፯፡፲፫–፳፬።
ከዘፍጥረት ፲፯፡፲፯–፲፰ ጋር አነጻፅሩ

አብርሐም የይስሀቅ መወለድ በተተነበየበት ጊዜ ተደ ሰተ እና ለእስማኤልም ጸለየ።

፲፫ አብርሃምም በግምባሩ ወደቀ እናም ተደሰተ፣ በልቡም አለ፣ የመቶ ዓመት ሰው በውኑ ልጅ ይወልዳል፣ እና ዘጠና ዓመት የሆናትም ሣራ ትወልዳለች።

፲፬ አብርሃምም እግዚአብሔርን አለው፣ እስማኤል በፊትህ በቅንነት ቢኖር በወደ ድሁ ነበር!

ጆ.ስ.ት.፣ ዘፍጥረት ፲፱፡፩–፲፭።
ከዘፍጥረት ፲፱፡፩–፲ ጋር አነጻፅሩ

ሎጥ የሰዶምን ክፋት ተቋቋመ፣ እናም መላዕክት ጠበ ቁት።

፩ እነርሱም ወዲያ ሂድ አሉት። እና ተናደውበትም ነበር።

፲ እና እርስ በራሳቸውም እንዲህ አሉ፣ ይህ ሰው በመካከላችን በእንግድነት ለመኖር መጣ፣ አሁን እራሱን ዳኛ ያደርግ ዘንድ ይፈልጋል፤ አሁን በእርሱ ላይ ከእ ነርሱ ይልቅ ክፉ እናደርግበታለን።

፲፩ ስለዚህ ለሰውየውም እንዲህ አሉት፣ ወንዶቹን፣ እና ደግሞ ሴት ልጆችህንም እንወስዳለን፤ እና መልካም እንደሚመ ስለን እናደርግባቸዋለን።

፲፪ አሁን ይህም በሰዶም ክፉነት በኩል ነበር።

፲፫ እና ሎጥም አለ፣ አሁን እነሆ፣ ወን ድን ያላወቁ ሁለት ሴቶች ልጆች አሉኝ፤ እባካችሁ፣ እነርሱን ወደ እናንተ ወደ ወን ድሞቹ እንዳላወጣላችሁ እለምናችኋለሁ፣ እና በአይኖቻችሁ መልካም እንደመሰላች ሁም አታደርጉባቸውም፤

፲፬ እግዚአብሔር አገልጋዩ በዚህ ነገር ተገቢ አያደርገውምና፤ ስለዚህ፣ ለዚህ አንድ ጊዜ፣ በእነዚህ ሰዎች ብቻ ምንም አታድርጉ፣ በቤቴም ሰላም እንዲኖራቸው ዘንድ እናንተን ወንድሞቼን እለምናችኋ ለሁ፤ እነርሱ በጣራዬ ጥላ ሥር የገቡበት ምክንያት ነውና።

፲፭ እና እነርሱም በሎጥ ተናድደው ነበር እና የደጁንም መዝጊያ ለመስበር ቀረቡ፣ ነገር ግን ቅዱስ ሰዎች የነበሩት የእ ግዚአብሔር መላእክቶች እጃቸውን ዘርግ ተው ሎጥን ወደ እነርሱ ዘንድ ወደ ቤት አገ ቡት መዝጊያውንም ዘጉት።

ጆ.ስ.ት.፣ ዘፍጥረት ፳፭፡፡፳–፳፱።

ዘፍጥረት ፳፭፡፡፳–፳፩ ጋር አነጻፅሩ

አብርሐም የዘለአለም እግዚአብሔርን አመለከ።

፳፩ አቢሜሌክና የሙሽራው ወዳጅ አኮዘት የሠራዊቱ አለቃ ፊኮልም ተነሥ ተው፣ እናም በቤርሳቤህ የተምር ዛፍን ተከሉ፣ እና በዚያ የጌታን ስም ጠሩ፤ ወደ ፍልስጥኤም ምድር ተመለሱ።

፳፪ እና አብርሐምም የዘላለሙን አም ላክ እግዚአብሔር አመለከ፣ እናም በፍ ልስጥኤም ምድር ብዙ ቀን እንግዳ ሆኖ ተቀመጠ።

ጆ.ስ.ት.፣ ዘፍጥረት ፳፯፡፡፲–፲፭።

ከዘፍጥረት ፳፯፡፡፲–፲ ጋር አነጻፅሩ

ኤፍሬም እና ምናሴ የእስራኤል ጎሳዎች ሆኑ። በጥንት ይኖር የነበረው ዮሴፍ ቤተሰቦቹን በጊዜው እንዳዳና ቸው፣ የእርሱ ትውልዶችም በኋለኛው ቀናት እስራኤ ልን በመንፈስ ያድናሉ።

፲ አሁንም እኔ ወደ አንተ ከመምጣቴ በፊት በግብፅ ምድር ስለተወለዱልህ ሁለቱ ልጆችህ ኤፍሬምና ምናሴ፣ እነሆ እነርሱ የእኔ ናቸው፣ እና የአባቶቼ አምላክ ይባ ርካቸዋል፤ እንዲሁም እንደ ሮቤልና እንደ ስምዖን ይባረካሉ፣ እነርሱ የእኔ ናቸውና፤ ስለዚህ በስሜም ይጠራሉ። (ስለዚህ እነ ርሱም እስራኤል ተብለው ተጠርተው ነበር።)

፲፩ እና ከእነርሱ በኋላ የወለድካቸው ልጆ ችህም የአንተ ይሆናሉ፣ እና በውርሳቸው፣ በጎሳዎቻቸውም፣ በወንድሞቻቸው ስም ይጠራሉ፤ ስለዚህ የምናሴና የኤፍሬም ጎሳ ተብለው ይጠራሉ።

፲፪ እና ያዕቆብ ዮሴፍን አለው፣ የአባ ቶቼ አምላክ በከነዓን ምድር በሎዛ ሲገለ ጥልኝ፣ ይህን መሬት ለዘለአለም ንብረት ለእኔ እና ለዘሬ እንደሚሰጠኝ ማለልኝ።

፲፫ ስለዚህ፣ ልጄ ሆይ፣ አንተ ቤቴን ከምት በማዳን ለእኔ አገልጋይ እንደት ሆን በማስነሳቱ ባርኮኛል።

፲፬ ህዝቦቼን፣ ወንድሞችህን፣ በምድሩ በሀይል ከነበረው ራብ ጊዜ በማዳን፤ ስለ ዚህ የአባቶችን አምላክ ይባርክሀል፣ እና የወገብህ ፍሬዎች፣ ከወንድሞችህ በላይ፣ እና ከአባትህ ቤት በላይ ይባረካሉ።

፲ አንተ አሸንፈሀልና፣ እና የአባትህም ቤት፣ ወደ ግብፅ በወንድሞችህ እጆች ከመሸጥህ በፊትአንተ ታይተውህ እንደ ነበረም፣ ለአንተ ሰገዱ፤ ስለዚህ ወንድሞ ችህ ለአንተ ከትውልድ ወደ ትውልድ፣ ለወገቦችህ ፍሬዎች ለዘለአለም ይሰግዳሉ፤

፲፩ ለህዝቦቼም፣ በባርነታቸው ቀን

ከአገልጋይነት እንድታድናቸው፣ ብርሀን ትሆናለህ፤ እና በጎጥያት ስርም አብረው ታጥፈው በነበረ ጊዜምደህንነትን እንድ ታመጣላቸው።

ጆ.ስ.ት.፣ ዘፍጥረት ፶፣ ፳፩–፳፰።

ከዘፍጥረት ፶፣ ፳፩–፳፮፤ ከ፪ ኔፊ ፫፣ ፬–፳፪ ጋር አነጻፅሩ

ጆሴፍ በግብፅ ውስጥ ሙሴ እስራኤልን ከግብጻዊ ባር ነት ነጻ እንደሚያደርግ፤ የጆሴፍ ትውልዶች ቅርን ጫፍ በጌታ ቃል ኪዳኖች ወደሚታወሱበት ወደ ሩቅ አገር እንደሚመሩ፤ እግዚአብሔር የይሁዳንና የዮሴ ፍን መዝገቦች እንዲያዋህድ ዮሴፍ የሚባል ነቢይ በኋ ለኛው ቀናት እንደሚጠራ፤ እና አሮን እንደ ሙሴ ተናጋሪ እንደሚያገለግል ተነበየ።

፳፩ እና ዮሴፍ ለወንድሞቹ አለ፣ እምታ ለሁ፣ እና ወደ አባቶቻችንም እሄዳለሁ፤ እና ወደ መቃብሬም በደስታ እሄዳለሁ። በባርነታችሁ ቀናት ከስቃያችሁ ያድናችሁ ዘንድ የአባቴ ያዕቆብ አምላክም ከእናንተ ጋር ይሁን፤ ጌታ ጎብኝቶኛል፣ እና ከወገቤ ፍሬዎች፣ ጌታ አምላክ ከወገቤ ጻድቃዊ ቅርንጫፍ ያስነሳ ዘንድ የጌታን ቃል ኪዳን አግኝቻለሁ፤ እና ለእናንተም፣ አባቴ ያዕ ቆብ እስራኤል ብሎ የጠራችሁ፣ ነቢይ፤ (ሻይሎ የሚባለው መሲህ አይደለም)፤ እና ይህም ነቢይ በባርነታችሁ ቀናት ህዝቦቼን ከግብፅ ያድናቸዋል።

፳፪ እናም እንዲህ ሆኖ አለፈ እንደገ ናም ይበተናሉ፤ እና ቅርንጫፍም ይሰበ ራል፣ እና ወደ ሩቅ አገርም ይወሰዳሉ፤ ይሁን እንጂ መሲህ ሲመጣ፣ በጌታ ቃል ኪዳን ይታወሳሉ፤ በኋለኛው ቀናት እርሱ በመንፈስ ኃይል ይገለጥላቸዋልና፣ እና ከጨለማ ወደ ብርሃን፣ ከተደበቀው ጨለ ማና ምርኮም ወደ ነፃነት ያወጣቸዋል።

፳፫ ጌታ አምላኬ፣ ለወገቤ ፍሬ ተመ ራጭ ባለራዕይ የሆነ ባለራዕይ ያስነሳል።

፳፬ እንደዚህም የአባቶቼ ጌታ አም ላክ አለኝ፣ ከወገብህ ፍሬ ምርጥ ባለራ ዕይ አስነሳለሁ፣ እርሱ ከወገብህ ፍሬ መካ ከል የተከበረ ይሆናል። ለእነርሱ፣ ለወን ድሞችህ፣ ታላቅ ስራን ይሰራ ዘንድ ትዕ ዛዝን እሰጠዋለሁ።

፳፭ ከአባቶችህ ጋር የገባሁትን ቃል ኪዳን እንዲያውቁት ያደርጋል፤ እና እን ዲሰራ ያዘዝኩትን ማንኛቸውን ነገሮችን ያደርጋል።

፳፮ በፊቴ ትልቅ አደርገዋለሁ፣ የእ ኔን ስራ ይሰራልና፤ እና የእስራኤል ቤት ሆይ፣ ህዝቦቼን ከግብፅ ምድር ነፃ ያወ ጣቸው ዘንድ አስነሳዋለሁ ብዬ ለእናንተ የተናገርኩለት ታላቅ ይሆናል፣ ከግብፅ ምድር ህዝቦችህን እንዲያወጣ ባለራዕይ አስነሳለሁና፤ እና እርሱም ሙሴ ተብሎ ይጠራል። እና በስሙም እርሱ ከእናንተ ቤት እንደሆነም ታውቁታላችሁ፤ በንጉስ ሴት ልጅ ይጠባል፣ እና ልጄም ተብሎ ይጠራልና።

፳፯ እንደገናም ባለራዕይ ከወገብህ ፍሬ አስነሳለሁ፤ እናም ለእርሱም ለወገብ ዘርህ ቃሌን ያመጣ ዘንድ ኃይልን እሰጠዋለሁ፤ እናም ጌታ እንዲህ አለ፥ ቃሌን ብቻ ለማ ምጣት ሳይሆን፣ ነገር ግን በመጨረሻው ቀናት በመካከላቸው የሄዱትን ቃሌን እን ዲያሳምን ነው።

፳፰ ስለሆነም፣ የወገብህ ፍሬዎች ይፅ ፋሉ፤ እናም የአይሁዳ የወገቡም ፍሬ ይፅ ፋሉ፤ እናም ይህ በወገብህ ፍሬ የሚጻ ፈው፣ ደግሞም በአይሁዳ ፍሬ የሚጻ ፈው፣ የውሸት ትምህርቶች ሀሰት መሆ ናቸውን ለማስረዳት፣ እና ፀብን እማቆም፣ እና በወገብህ ፍሬ መካከል ሰላምን ለመ መስረት፣ እና በኋለኛው ቀናት ወደ አባ ቶቻቸው ግንዛቤ፣ እናም ደግሞ ለቃል ኪዳናቴ ግንዛቤ ለማምጣት በአንድ ላይ ያድጋሉ ይላል ጌታ።

፳፱ እናም በመጨረሻው ቀናት የሚ መልሳቸው ስራዬ የእስራኤል ቤት በሆ ኑት በሁሉም ህዝቦቼ መካከል በሚሄድበት ጊዜ፣ እርሱ ከድካም ይበረታል።

፳፲ ባለራዕዩን ጌታ ይባርከዋል፣ እናም እርሱን ለማጥፋት የሚሞክሩ ይሸነፋሉ፣ ይህን ቃል ኪዳን እሰጥሀለሁና፤ ከትው

ልድ እስከትውልድ አስታውስሀለሁ፣ እና ስሙም ዮሴፍ ተብሎ ይጠራል፣ ስሙም ከአባቱም ጋር አንድ ይሆናል፣ እናም እርሱ ልክ እንደአንተ ይሆናል፣ ጌታ በእርሱ እጅ የሚያመጣው ነገር ህዝቦቼን ወደ ደህንነት የሚያመጣ ይሆናልና።

፴፬ እና ጌታ ዮሴፍን ለዘለአለም ፍሬውን እንደሚጠብቅ ቃል ገብቶለት አለ፣ ሙሴን አስነሳለሁ፣ እና በእጁም በትር ይኖራል፣ እና እርሱም ህዝቦቼን ይሰበስባል፣ እና እንደ መንጋዎችም ይመራቸዋል፣ እና የቀይ ባህር ውሀንም በበትሩ ይመታል።

፴፭ እና ፍርድም ይኖረዋል፣ እና የጌታን ቃል ይፅፋል። እና ብዙ ቃላቶችንም አይናገርም፣ በራሴ እጅ ጣት ህጌን እፅፍ ለታለሁና። እናም ተናጋሪ እሰጠዋለሁ፣ እና ስሙም አሮን ተብሎ ይጠራል።

፴፮ እና ደግሞም መሀላ እንደገባሁትም በመጨረሻው ቀናት ይህ ለአንተ ይሆንልሀል። ስለዚህ፣ ዮሴፍ ለወንድሞቹ እንዲህ አለ፣ እግዚአብሔርም በእርግጥም ይጎበኛችኋል፥ ከዚህችም ምድር ያወጣችኋል፤ ለአብርሃምና ለይስሐቅ ለያዕቆብም ወደ ማለላቸው ምድር ያደርሳችኋል።

፴፯ እና ዮሴፍ ለወንድሞቹ ብዙ ሌላ ነገሮች አረጋገጠ፣ እና እግዚአብሔር በእርግጥም ሲጎበኛችሁ አጥንቴን ከዚህ አንሥታችሁ ከእናንተ ጋር ትወስዳላችሁ ብሎ የእስራኤልን ልጆች መሀላ ገባ።

፴፰ ዮሴፍም በመቶ አሥር ዓመት ዕድሜው ሞተ፤ በሽቶም አሹት፥ በግብፅ ምድር በሣጥን ውስጥ አኖሩት፤ እና እንዲወሰድ እና በአባቱ መቃብር ውስጥ እንዲቀበር ዘንድ፣ የእስራኤል ልጆችም እርሱን ከመቀበር አስቀሩት። እና እንደዚህም ለእርሱ የማሉትን መሀላ አስታወሱ።

ጆ.ስ.ት.፣ ዘፀአት ፤፡ ፳፤፡ ከዘፀአት ፤፡ ፳፩፤ ፲፯፡ ፲፰፡ ፲፱፡ ፳፡ ፳፩፡ ፳፡ ፲፯፤ ከዘዳግም ፪፡ ፴ ጋር አነጻፅሩ

ጌታ ለፈርዖን ልብ መፅናት ሀላፊ አይደለም። ደግሞም ጆ.ስ.ት.፣ ዘፀአት ፯፡ ፲፫፣ ፲፫፣ ፱፡ ፲፪፣ ፲፡ ፩፣ ፳፣ ፳፯፣ ፲፩፡ ፲፣ ፲፬፡ ፡ ፳፡ ፲፯ን ተመልከቱ፣ እያንዳንዱ ማጣቀሻዎች፣ በትክክል ሲተረጎሙ፣ ፈርዖን የራሱን ልብ እንዳጸና ያሳያሉ።

፳፩ እግዚአብሔርም ሙሴን አለው፣ ወደ ግብፅ ስትመለስ በእጅህ ያደረግሁትን ተአምራት ሁሉ በፈርዖን ፊት ታደርገው ዘንድ ተመልከት፣ እና እኔም ውጤታማ እንድትሆን አደርግሀለሁ፤ ፈርዖን ግን ልቡን ያጸናዋል፣ እና ሕዝብንም አይለቅም።

ጆ.ስ.ት.፣ ኦሪት ዘፀአት ፤፡ ፳፩–፳፯። ከዘፀአት ፤፡ ፳፩–፳፯ ጋር አነጻፅሩ

ሙሴ ወንድ ልጁን ባለመግረዙ ምክንያት ጌታ ሊገድለውም ሲያስፈራራ፣ ሲፓራም ይህን ስርዓት እራሷ በማከናወን ህይወቱን አዳነች። ሙሴም ኃጢያቱን ተናዘዘ።

፳፪ እንዲህም ሆነ፤ በመንገድ ላይ ባደረበት ሰፍራ እግዚአብሔር ተገናኘው። የጌታ ቁጣ በሙሴ ላይ ነደደ፣ እናም ሊገድለውም እጁ ሊያሳርፍበት ነበር፤ ምክንያቱም ወንድ ልጁን አልገረዘምና።

፳፫ ከዚያም ሲፓራም ባልጩት ወሰደች፥ የልጅዋንም ሸለፈት ገረዘች፥ እናም ባልጩትን ወደ እግሩም ጣለችው፣ እና በእርግጥም አንተ ለእኔ የደም ሙሽራ ነህ አለች።

፳፬ እናም ጌታ ሙሴን አዳነው እናም ለቀቀው፣ ምክንያቱም ሲፓራም ሚስቱ ልጅን ስለገረዘች። ስለ ግርዛቱ አንተ የደም ሙሽራ ነህ አለች። እና ሙሴ አፈረ፣ እና ፊቱን ከጌታ ሸሸገ፣ እናም አለ፣ በጌታ ፊት ኃጢያት ሰርቻለሁ።

፳፭ እግዚአብሔርም አሮንን፣ ሄደህ በምድረ በዳ ሙሴን ተገናኘው አለው፤ ሄዶም በእግዚአብሔር ተራራ ተገናኘው፤ እግዚአብሔር ለእርሱ በታየበት ተራራም ላይ፣ እና አሮን ሳመውም።

ጆ.ስ.ት.፣ ዘፀአት ፲፰፡፩። ከዘፀአት ፲፰፡፩ ጋር አነጻፅሩ

ዮቶር ሊቀ ካህን ነው።

፩ የምድያምም ሊቀ ካህን የሙሴ አማት ዮቶር እግዚአብሔር ለሙሴና ለሕዝቡ ለእስራኤል ያደረገውን ሁሉ፣ እግዚአብሔርም እስራኤልን ከግብፅ እንዳወጣ ሰማ፤

ጆ.ስ.ት.፣ ዘፀአት ፳፪፡፲፰። ከዘፀአት ፳፪፡፲፰ ጋር አነጻፅሩ

ገዳዮች አይኖሩም።

፲፰ ገዳይ እንዲኖር አትፍቀዱለት።

ጆ.ስ.ት.፣ ኦሪት ዘፀአት ፴፪፡፲፬። ከዘፀአት ፴፪፡፲፬ ጋር አነጻፅሩ

ጌታ ንስሀ የሚገቡትን እስራኤላውያንን ያተርፋል።

፲፬ እናም ጌታም ሙሴን አለው፣ ክፉ ላደረጉት ንስሀ ከገቡ፣ እንዲሁ እምራቸ ዋለሁ፣ እናም ከፍተኛ ቁጣዬን ከእነርሱ አዞራለሁ፤ ነገር ግን፣ እነሆ፣ በዚህ ቀን ለተደረገው ለዚህ ክፉት ንስሀ ባልገቡት ላይ ሁሉትፈርዳለሀ። ስለዚህ፣ ያዘዝኩህን ነገር ለማድረግ ታረጋግጣለህ፣ ወይም በሕዝቤ ላይ ላደርግ ያሰብኩትን በሙሉ አከናውናለሁ።

ጆ.ስ.ት.፣ ዘፀአት ፴፫፡፳፣ ፳፫፡፡
ከዘፀአት ፴፫፡፳፣ ፳፫፡ ጋር አነጻፅሩ

ማንም ጎጥያተኛ ሰው የእግዚአብሔርን ፊት ማየት እና መኖር አይችልም።

፳ እና ሙሴን እንዲህ አለው፣ ፊቴን በዚህ ጊዜ ልታየኝ አትችልም፣ አለበለዚያ ቁጣዬ በአንተ ላይ ደግማም ትቀጣጠላለች፣ እና አንተንና ህዝቦችህን አጠፋለሁ፤ በዚህ ጊዜ በመካከላቸው ማንም ሰው አይቶኝ አይኖርምና፣ በጣም ጎጥያተኞች ናቸውና። እና ማንም ጎጥያተኛ ሰው በምንም ጊዜ ፊቴን አይቶ፣ ወይም ማንም ጎጥያተኛ ሰው በምንም ጊዜ ፊቴን በማየት፣ እና ለመኖር አይችልም።

፳፫ እና እጄንም ፈቀቅ አደርጋለሁ፣ ጀርባዬንም ታያለህ፣ ፊቴን ግን እንደሌላው ጊዜ አይታይም፤ በህዝቦቼ እስራኤል ተናድጃለሁና።

ጆ.ስ.ት.፣ ዘፀአት ፴፬፡፩–፪፣ ፲፩፡፡
ከዘፀአት ፴፬፡፩–፪፣ ፲፩፡ ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች ፲፱፡፩–፳፯ ጋር አነጻፅሩ

እግዚአብሔር እንደገና ህግን በሙሴ በተዘጋጀ ድንጋይ ላይ ጻፈ እናም የመልከ ጼዴቅ ክህነትና ስርዓቶችን ከእስራኤል ህዝብ ወሰደ። በዚህ ምትክም የስጋዊ ትእዛዛት ህግን ሰጣቸው።

፩ እና ጌታ ሙሴን አለ፣ እንደመጀመሪያው አይነት ሁለት የድንጋይ ጽላቶች ጥረብ፣ እና በእነርሱም ላይ ደግሜ የህግን ቃላቶች አንተ በሰበርካቸው በመጀመሪያው ጽላቶች ላይ በተጻፉበት መሰረት እፅፍባቸ ዋለሁ፤ ነገር ግን በመጀመሪያው መሰረት አይሆኑም፣ ከመካከላቸው ክህነትን እወስዳለሁና፤ ስለዚህ ቅዱስ ስርዓት፣ እና የዚህ ስነ ስርዓት፣ በፊታቸው አይሄድምና፤ እኔም በመካከላቸው አልሄድምና፣ አለበለዚያ አጠፋቸዋለሁ።

፪ ነገር ግን እንደ መጀመሪያውም ህግን እሰጣቸዋለሁ፣ ነገር ግን ይህም የስጋዊ ትእዛዝ ህግ ይሆናል፤ በቁጣዬ በእንግድነታቸው ዘመን ወዳለሁበት፣ ወደ እረፍቴ እንዳይገቡ መሀላ ገብቼአለሁ። ስለዚህ እንዳዘዝኩህ አድርግ፣ እና በጠዋትም ተዘጋጅ፣ እና በጠዋት ወደ ሲና ተራራ ውጣ፣ እና በፊቴም በተራራው ጫፍ ላይ ራስህን አቅርብ።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የብሉይ ኪዳን ህዝቦች የሚያ ውቁበት አንድ ስም ያህዌህ ነው።

፲፩ ስሙ ያህዌህ፣ ቀናተኛ የሆነ እግዚአብሔር ነውና ለሌላ አምላክ አትስገድ።

ጆ.ስ.ት.፣ ዘዳግም ፲፡፪። ከዘዳግም ፲፡፪ ጋር አነጻፅሩ

በመጀመሪያው ጽላቶች ላይ እግዚአብሔር የቅዱስ ክህነት ዘለአለማዊ ቃል ኪዳንን ገለጸ።

፪ ከቅዱስ ክህነት ዘለአለማዊ ቃል

ኪዳን ቃላቶች በስተቀር፣ በሰበርሃቸውም በፊተኞቹ ጽላቶች የነበሩትን ቃሎች በእነ ዚህ ጽላቶች እጽፋለሁ፥ በታቦቱም ውስጥ ታደርጋቸዋለህ።

ጆ.ስ.ት.፣ ፮ ሳሙኤል ፲፮፥፲፬–፲፯፣ ፳፫። ከ፮ ሳሙኤል ፲፮፥፲፬–፲፯፣ ፳፫ ጋር አነጻፅሩ፤ በ፮ ሳሙኤል ፲፭፥፲ እና ፲፱፥፱ ላይም አንድ አይነት ቅያሬዎች ተደርገዋል

በሳኦል ላይ የመጣው የክፉ መንፈስ ከጌታ አልነበረም።

፲፬ የእግዚአብሔርም መንፈስ ከሳኦል ራቀ፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ ያልመጣው ክፉም መንፈስ አሠቃየው።

፲፭ የሳኦልም ባሪያዎችም አሉት፣ እነሆ ከእግዚአብሔር ዘንድ ያልሆነው ክፉ መን ፈስ ያሠቃይሃል።

፲፮ በገና መልካም አድርጎ የሚመታ ሰው ይሹ ዘንድ ጌታችን በፊቱ የሚቆሙ ትን ባሪያዎቹን ይዘዝ፤ ከእግዚአብሔርም ዘንድ ያልመጣው ክፉ መንፈስ በሆነብህ ጊዜ በእጁ ሲመታ አንተ ደኅና ትሆናለህ።

፳፫ እንዲህም ሆነ፤ ከእግዚአብሔር ዘንድ ያልመጣው ክፉ መንፈስ በሳኦል ላይ በሆነ ጊዜ ዳዊት በገና ይዞ በእጁ ይመታ ነበር፤ ሳኦልንም ደስ ያሰኘው ያሳርፈውም ነበር፣ ክፉ መንፈስም ከእርሱ ይርቅ ነበር።

ጆ.ስ.ት.፣ ፮ ሳሙኤል ፲፮፥፲፫። ከ፮ ሳሙኤል ፲፮፥፲፫ ጋር አነጻፅሩ

የዳዊት አሰቃቂ ኀጥያት በእግዚአብሔር አልተረሣም።

፲፫ ዳዊትም ናታንን፣ እግዚአብሔ ርን በድያለሁ አለው። ናታንም ዳዊትን፣ እግዚአብሔር ደግሞ ኃጢአትህን አል ረሣልህም፤ አትሞትም።

ጆ.ስ.ት.፣ መፅሐፈ ዜና ቀዳማዊ ፳፭፥፲፭። ከመፅሐፈ ዜና ቀዳማዊ ፳፭፥፲፭ ጋር አነጻፅሩ

መልአኩ ኢየሩሳሌምን እንዳይደመስስ እግዚአብሔር አቆመው።

፲፭ እግዚአብሔርም ያጠፋት ዘንድ ወደ ኢየሩሳሌም መልአኩን ሰደደ። እናም መልአኩ ኢየሩሳሌምን ለማጥፋት እጁን አንሳ፣ እናም እግዚአብሔር ለመልአኩ፣ በቃህ፤ አሁን እጅህን መልስ አለው፤ ሊያ ጠፋትም በቀረበ ጊዜ፣ ጌታ እስራኤል ስለ ክፉው ነገር ተጸጽታ እንደነበር አየ፤ ስለ ዚህ በኢያቡሳዊው በኦርና አውድማ አጠ ገብ ቆሞ የነበረውን የሚያጠፋውንም መል አኩ ጌታ አቆመው።

ጆ.ስ.ት.፣ መፅሐፈ ዜና ካልዕ ፲፰፥፳፪። ዜና መዋዕል ካልዕ ፲፰፥፳፪ ጋር አነጻፅሩ

ጌታ በነብያት አፎች ውስጥ የሀሰት መንፈስ አያስገ ባም።

፳፪ አሁንም ስለዚህ፣ እነሆ፣ ጌታ በእ ነዚህ በነቢያትህ አፍ ሐሰተኛ መንፈስን አገኘ፤ ጌታ በአንተ ላይ ክፉ ተናግሮብሃል።

ጆ.ስ.ት.፣ መዝሙር ፲፭፥፭–፰። ከመዝሙር ፲፭፥፭–፰ ጋር አነጻፅሩ

በመጨረሻው ቀናት ጻድቃን ወደ ጌታ ተራራ ይሸ ሻሉ። ጌታ ሲመጣም፣ ክፉውን ያጠፋል እናም ጻድቁን ያቤዛል።

፭ አንተ በምትመጣበት በዚያ ቀን፣ አቤቱ ጌታ፤ እናም እምነቴን በአንተ ላይ እጥላለሁ። ለህዝብህም ትላለህ፣ ጆሮዬ ድምጽህን ሰምቷልና፤ ለእያንዳንዱም ነፍስ ትላለህ፣ ወደ ተራራዬ ሽሹ፤ እናም ጻድቃን ከወፍ ወጥመድ እንደተለቀቀች ወፍ ይሸሻሉ።

፮ ኃጢአተኞች እነሆ ቀስታቸውን ገትረ ዋልና፥ ፍላጻቸውንም በአውታር አዘጋጅ ተዋልና፥ ልበ ቅኖችን በስውር ይነድፉ፣ መሰረታቸውን ይደመስሱ ዘንድ።

፯ ነገር ግን የክፉ መስረት ይደመሰሳ ልና፣ እናም ምን ለማድረግ ይችላሉ?

፰ ጌታ ወደተቀደሰው መቅደሱ ሲመጣ፤ በእግዚአብሔር ዙፋን ላይ በሰማይ ተቀ ምጦ፣ ዓይኖቹ ክፉዎችን ይመረምራሉ።

፱ እነሆ አይኖቹ የሰው ልጆችን ይመረ ምራሉ፣ እናም ጻድቃንን ያድናል፣ እናም

እነርሱም ይመረመራሉ። ጌታ ጻድቅን ይወዳል፣ ዓመፃን የወደዳት ኅጥእን ግን ነፍሱን ጠልቶአል።

ጆ.ስ.ት.፣ መዝሙር ፲፩፡፩–፯።
ከመዝሙር ፲፩፡፩–፯ ጋር አነጻፅሩ

መዝሙረኛው በመጨረሻዎቹ ቀናት እውነቶች እንደ ሚጠፉ ተመለከተ እናም የፅዮን በዳግም መመስረትን በጉጉት ጠበቀ።

፩ ሰነፍ በልቡ *አምላክን ያየ ማንም ሰው የለም ይላል። ለእኛ እራሱን ስለማያሳይ፣ አምላክ የለም። እነሆ፣ የረከሱ ናቸው፤ የሚያስጸይፍ ስራዎች ሰርተዋል፣ እና ማን ኛቸውም በጎ ነገርን አይሰሩም።*

፪ *እግዚአብሔር ከሰማይ የሰው ልጆችን ተመለከቷል፣ እና በድምጹም ለአገልጋ ዮቹ እንዲህ አለ፣ እግዚአብሔር የሚገባ ቸው ማንኛቸውም እንዳሉ ከሰዎች ልጆች መካከል ፈልጉ። እና እርሱም አቆን ወደ ጌታ ከፈተ፣ እናም አለ፣ እነሆ፣ ይህን የሚሉ ሁሉ የአንተ ናቸው።*

፫ *ጌታም መለሰ፣ እና አለ፣ ሁሉ ዐመፁ፣ በአንድነትም የረከሱ ናቸው፣ በጎ ነገርን የሚሠራ እንደሌለም ታያለህ፤ አን ድም ስንኳ የለም።*

፬ *ለአስተማሪ ያላቸው ሁሉ የርኩስ ሰራ ተኞች ናቸው፣ እና በውስጣቸውም ምንም እውቀት የለም። እነርሱም ህዝቦቼን የሚ በሉት ናቸው። እንጀራን ይበላሉ እና ጌታ ንም አይጠሩትም።*

፭ *በታላቅ ፍርሀት ውስጥ ናቸው፣ እግ ዚአብሔር በጻድቃን ትውልዶች መካ ከል ይኖራልና። እርሱም የደሀዎች አማ ካሪ ነው፣ ምክንያቱም በክፉዎች አፍረ ዋል፣ እና ለመሸሸጊያቸውም ወደ ጌታ ይሸሻሉ።*

፮ *በደሀ ምክር ያፈሩ ናቸው ምክንያቱም ጌታ መሸሸጊያው ነውና።*

፯ *ኦ ፅዮን፣ የእስራኤል መድሀኒት፣ ከሰ ማይ ብትመሰረት ኖሮ። አቤቱ ጌታ፣ ፅዮ ንን መቼ ትመሰርታለህ? ጌታ ህዝቡን ከባ ርነት መልሶ ሲያመጣ፣ ያዕቆብ ይደሰታል፣ እስራኤልም ደስተኛ ትሆናለች።*

ጆ.ስ.ት.፣ መዝሙር ፹፬፡፩–፲፩።
ከመዝሙር ፹፬፡፩–፲ ጋር አነጻፅሩ

የክብር ንጉስ በሚመጣበት ጊዜ ህዝቡን ይቤዣቸዋል።

፩ *ራሶቻችሁን ከፍ አድርጉ፣ የያዕቆብ ትውልዶች ሆይ፤ እና ወደላይ ከፍ ተደ ረጉ፤ እና ክብር ንጉስ የሆነው ብርቱና ኃያል ጌታ፣ በሰልፍ ኃያል ጌታ ለዘለአለም ይመ ሰርታችኋል።*

፪ *እና ሰማይን ይጠቀልላል፤ እና ህዝቦ ቹን ለማዳን፣ የዘለአለም ስም ለመስራት፣ በዘለአለም ስለቱ ላይ እንዲመሰርታችሁ ይወርዳል።*

፫ *ራሶቻችሁን ከፍ አድርጉ፣ የያዕቆብ ትውልድ ሆይ፤ ራሶቻችሁን ከፍ አድ ርጉ፣ የዘለአለም ትውልዶች ሆይ፤ እና የሰራዊት ጌታ፣ የነገሥታት ንጉሥ፤*

፬ *እንዲሁም የክብር ንጉስ ወደ እናንተ ይመጣል፤ እና ህዝቦቹን ያድናል፣ እና በጻድቅነትም ይመሰርታቸዋል። ሰላህ*

ጆ.ስ.ት.፣ መዝሙር ፹፭፡፩።
ከመዝሙር ፹፭፡፩ ጋር አነጻፅሩ

ለጠላቶቻችን መጸለይ ይገባናል።

፩ *እና ምንም እንኳ ብወዳቸውም፣ ጠላቶቼ ናቸው፤ እኔ ግን ለእነርሱ መጸ ለይ እቀጥላለሁ።*

ጆ.ስ.ት.፣ ኢሳይያስ ፹፱፡፩–፳።
ከኢሳይያስ ፹፱፡፩–፳ ጋር አነጻፅሩ

በኢየሩሳሌም ከበፊት በጥንት ነቢያት የተሰበከው መልእክት በበኋለኛው ቀናት "ከምድር ውስጥ" በሚ መጣው በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ ይሰበካል።

፩ ዳዊት ለሰፈረባት ከተማ ለአርኤል ወዮላት! ዓመት በዓመት ላይ ጨምሩ፤ በዓላትም ይመለሱ።

፪ *አርኤልንም አስጨንቃለሁ፥ ልቅሶና ዋይታም ይሆንባታል፤ ጌታም እንዲህ ብሎኛል፣ እንደ አርኤልም ትሆንልኛለች።*

፫ *በዙሪያዋም እሰፍራለሁ፥ በቅጥርም*

ከብቤ አስጨንቃታለሁ፥ አምባም በላይዋ አቆማለሁ።

፪ ትዋረዳለች፥ በመሬትም ላይ ሆና ትና ገራለች፥ ቃሏም ዝቅ ብሎ ከአፈር ይወ ጣል፤ ድምጿም ከመሬት እንደሚወጣ እንደ መናፍስት ጠሪ ድምፅ ይሆናል፥ ቃሏም ከአፈር ወጥቶ ይጮኻል።

፫ ነገር ግን የጠላቶቿ ብዛት እንደ ደቀቀ ትቢያ፥ የጨካኞችም ብዛት እንደሚያልፍ ገለባ ይሆናል፤ አዎን፣ ድንገትም ፈጥኖ ይሆናል።

፬ በሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር በነጐ ድጓድ፥ በምድርም መናወጥ፥ በታላቅም ድምፅ፥ በዐውሎ ነፋስም፥ በወጨፎም፥ በምትበላም በእሳት ነበልባል ይጐበኛሉና።

፭ በአርኤልም ላይ የሚዋጉ፥ እርስዋንና ምሽግዋንም የሚወጉ የሚያስጨንቋትም፥ የአሕዛብ ሁሉ ብዛት እንደ ሕልምና እንደ ሌሊት ራእይ ይሆናል።

፮ አዎን፣ ለእነርሱም ተርቦም እንደሚ ያልም ሰው ይሆናል፣ እነሆ፥ ይበላል፥ ነገር ግን ይነቃል ሰውነቱም ባዶ ነው፤ ወይም ተጠምቶም እንደሚያልም ሰው ይሆናል፤ በሕልሙም፥ እነሆ፥ ይጠጣል፥ ነገር ግን ይነቃል፥ እነሆም፥ ይዝላል ሰውነቱም አምሮት አለው፤ አዎን፣ እንዲሁ የጽዮ ንን ተራራ የሚወጉ የአሕዛብ ሁሉ ብዛት ይሆናል።

፤ኢሳ.ት.፣ ኢሳይያስ ፵፪፥፲፱–፳፫። ከኢሳይያስ ፵፪፥፲፱–፳፪ ጋር አነጻፅሩ

ጌታ እውነትን ለማየት ወይም ለመስማት ያልመረጡ ትን ለማስተማር አገልጋዩን ይልካል፤ የሚያዳምጡና የሚታዘዙም ፍጹም ይሆናሉ።

፲፱ ዕውር ወደሆናችሁት፤ አዎን፣ የዕ ውሩን አይን ለመክፈት፣ እና የደንቆሮ ውን ጆሮዎች ለመክፈት አገልጋዬን እል ክልሀለሁ፤

፳ እና አይነ ስውር ቢሆኑም፣ መልእ ክተኛውን፣ የጌታን አገልጋይ፣ ካዳመጡ ፍጹም ይሆናሉ።

፳፩ እናንተ ህዝቦች ናችሁ፣ ብዙ ነገርን ታያላችሁ ነገር ግን አትጠባበቁትም፤ ጆሮ አችሁም ለመስማት ተከፍተዋል፣ ነገር ግን አትሰሙም።

፳፪ እግዚአብሔር በእንደዚህ አይ ነት ሰዎች አልተደሰተም፣ ነገር ግን ስለ ጽድቁ ሕጉን ታላቅ ያደርጋል እና የከበር ያደርገዋል።

፳፫ እናንተ የተበዘበዘና የተዘረፈ ሕዝብ ናችሁ፤ ጠላቶቻችሁ፣ ሁሉም፣ በዋሻዎች ውስጥ ጠምደዋችኋል፣ እና በእስር ቤትም ሸሽገዋችኋል፤ እንደ አደን አስበዋችኋል፣ እና ማንም አያድንም፤ እንደ ምርኮም፣ እና ማንም ደግሞ ይመለስ አላለም።

፤ኦ.ስ.ት.፣ ኤርምያስ ፳፯፥፲፫። ከኤርምያስ ፳፯፥፲፫ ጋር አነጻፅሩ

ጌታ ንስሀ አይገባም፤ ሰዎች ንስሀ ይገባሉ።

፲፫ ስለዚህ አሁን መንገዳችሁንና ሥራ ችሁን አሳምሩ፣ እና የአምላካችሁንም የእግዚአብሔርን ድምፅ ስሙ፣ እና ንስሀ ግቡ፣ እና ጌታም የተናገረባችሁን ክፉ ነገር ይተዋል።

፤ኦ.ስ.ት.፣ ዓሞጽ ፯፥፫። ከዓሞጽ ፯፥፫ ጋር አነጻፅሩ

ጌታ ንስሀ አይገባም፤ ሰዎች ንስሀ ይገባሉ።

፫ እና ጌታ ያዕቆብን በሚመለከት አለ፣ ያዕቆብ ለዚህ ንስሀ ይገባል፣ ስለዚህ ሙሉ በሙሉ አላጠፋውም።

፤ኦ.ስ.ት.፣ ማቴዎስ ፫፥፬–፮። ከማቴዎስ ፪፥፬–፮ ጋር አነጻፅሩ

ነቢያት ቤተ ልሔም መሲህ የሚወለድበት ቦታ እንደ ሆነ አቅድመው ተናገሩ።

፬ የካህናትንም አለቆች የሕዝቡንም ጻፎች ሁሉ ሰብስቦ እንዲህ በማለት ጠየቃ ቸው፥ ክርስቶስ ወዴት እንዲወለድ በነቢ ያት የተጻፈበት ቦታ የት ነው? ምክንያ ቱም ታላቅ ፍርሀት ነበረው፣ ግን በነቢ ያት አያምንም ነበር።

፭ እነርሱም በነቢይ እንዲህ ተጽፎአ

ልና፣ በይሁዳ ቤተ ልሔም ይወለዳል፣ እንደዚህ ብለዋልና አሉት፣

፤ የጌታ ቃል ወደ እኛ እንዲህ በማለት መጣ፣ እናም አንቺ ቤተ ልሔም፥ የይሁዳ ምድር፥ በአንቺ ውስጥ ከይሁዳ ገዢዎች ከቶ ታናሽ ያልሆነ መስፍን ይወለዳል፤ ሕዝቤን እስራኤልን የሚያድን መስፍን ከአንቺ ይወጣልና።

ጆ.ስ.ት.፣ ማቴዎስ ፫፥ ፳፰–፳፱።
ከማቴዎስ ፪፥ ፳፫ ጋር አነጻፅሩ

ኢየሱስ አደገ እናም አገልግሎቱን ከመጀመሩ በፊት ጌታን ጠበቀ።

፳፰ እና እንዲህ ሆነ ኢየሱስ ከወንድሞቹ ጋር አደገ፣ እና ጠነከረ፣ እና የአገልግሎቱ ጊዜ እስከሚመጣም ጌታን ጠበቀ።

፳፱ እና ከአባቱ በታች አገለገለ፣ እና እንደ ሌሎች ሰዎች አልተናገረም፣ ወይም ሊማርም አልቻለም፤ ምንም ሰው እንዲ ያስተምረው አላስፈለገውምና።

፳፤ እና ከብዙ አመቶች በኋላ፣ የአገል ግሎቱ ሰዓት ቀረበ።

ጆ.ስ.ት.፣ ማቴዎስ ፫፥ ፴፩–፴፤።
ከማቴዎስ ፫፥ ፲–፱ ጋር አነጻፅሩ

የመጥምቁ ዮሐንስ መልእክትን የማይቀበሉ ክርስቶ ስን አይቀበሉም። እግዚአብሔር ከእስራኤል ያልሆኑን የቃል ኪዳን ህዝቦች ለማድረግ ይችላል።

፴፩ እግዚአብሔር ራሱ የላከውን ስብ ከት ለምንድን ነው የማትቀበሉት? ይህብ በልባችሁ ካልተቀበላችሁ፣ እኔን አት ቀበሉም፤ እናም እኔን ካልተቀበላችሁ፣ እኔ እንድመሰክርበት የተላኩትን አትቀ በሉም፤ እናም ለኃጢያቶቻችሁ ምንም መሸፈኛ የላችሁም።

፴፫ እንግዲህ፣ ንስሀ ግቡ፣ ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አድርጉ፤

፴፤ በልባችሁም የአብርሐም ልጆች ነን እና ወደ አባታችን አብርሐም ፍሬ እናምጣ በማለት አታስቡ፤ እላችኋለሁና፣ ከነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ሊያስነሣለት እግዚአብሔር ይችላል።

ጆ.ስ.ት.፣ ማቴዎስ ፫፥ ፴፭–፴፯።
ከማቴዎስ ፫፥ ፲፩–፲፪ ጋር አነጻፅሩ

መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ እና በእሳት ለመጥመቅ ሀይል እንዳለው መስክሯል።

፴፭ እኔስ ንስሐ ከገባችሁ በኋላ በውኃ አጠምቃችኋለሁ፤ እናም ስለእርሱ ምስክር የምሰጠው፣ ጫማውን እሸከም ዘንድ የማ ይገባኝ፣ (ወይም በታውን ለሞምላት የማ ልችለው) ሲመጣ፣ እንዳልኩት፣ እርሱ ከመምጣቱ በፊት አጠምቃችኋለሁ፣ እርሱ ሲመጣም በመንፈስ ቅዱስ በእሳ ትም ያጠምቃችኋል።

፴፮ እና የምመሰክርበት፣ መንሹም በእጁ የሆነው እርሱ ነው፥ አውድማውንም ፈጽሞ ያጠራል፥ ስንዴውንም በጎተራው ይከታል፥ ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት በጊዜው ሙላት ያቃጥለዋል።

፴ በዚህም ዮሐንስ በዮርዳኖች ወንዝ በመስበክ እና በመጥመቅ መጣ፤ ከእር ሱም በኋላ የሚመጣው መንፈስ ቅዱስ እና በእሳት ለመጥመቅ ሀይል እንዳለው እየ መሰከረም።

ጆ.ስ.ት.፣ ማቴዎስ ፫፥ ፴፫–፴፮።
ከማቴዎስ ፫፥ ፲፫–፲፯ ጋር አነጻፅሩ

ዮሐንስ ኢየሱስን በማጥለቅ አጠመቀ፣ መንፈስ ቅዱስ እንደ ርግብ ሲወርድ አየ፣ እናም የአብን ድምፅ ሰማ።

፴፫ እና ኢየሱስም መልሶ፣ በአንተ እንድጠመቅ ፍቀድልኝ፣ እንዲህ ጽድ ቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና አለው። ያን ጊዜ ፈቀደለት።

፴፬ እና ዮሐንስ ወደ ውሀው ገባ እና አጠመቀው።

፴፭ ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውኃ ወጣ፤ ዮሐንስም አየ፣ እና አስተ ዋለ፣ ሰማያት ተከፍተውለት ነበር፣ እና የእ ግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወ ርድ በኢየሱስ ላይም ሲመጣ አየ፤

፴፮ አስተዋለም፣ ከሰማይም ድምፅ እን ዲህ ሲል ሰማ፣ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወ ደው ልጄ ይህ ነው። አድምጠው።

ጆ.ስ.ት.፣ ማቴዎስ ፪፡፭፣ ፮–፯፣ ፰–፱፡፡ ከማቴዎስ ፪፡፭፣ ፮–፯፣ ፰–፱ ጋር አነጻፅሩ፤ በሉቃስ ፪፡፪፣ ፮–፲፩ም እንደዚህ አይነት ቅያሬዎች ነበሩ

ኢየሱስ የተመራው በመንፈስ እንጂ በሰይጣን አይ ደለም።

፭ ከዚያ ወዲያ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር ይሆን ዘንድ መንፈስ ወደ ምድረበዳ ወሰደው።

፮ ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ወደ ቅድስት ከተማ ተወሰደ፣ እና መንፈስ እርሱን በመ ቅደስ ጫፍ ላይ አቆመው፡፡

፯ ከእዚያም በኋላ ዲያብሎስ ወደእርሱ መጣ እና እንዲህ አለው፣ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝልሃል እግርህንም በድንጋይ ከቶ እንዳትሰናከል በእጃቸው ያነሡሃል ተብሎ ተጽፎአልና የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንህ፣ ወደ ታች ራስህን ወርውር አለው፡፡

፰ ደግሞም፣ ኢየሱስ በመንፈስ ውስጥ ነበር፣ እና ይህም ወደ እጅግ ረጅም ወደ ሆነ ተራራ ወሰደው፣ የዓለምንም መንግሥታት ሁሉ ክብራቸውንም አሳየው፡፡

፱ እና ዲያብሎስም ወደ እርሱ እንደገና መጣ፣ እና አለው፣ ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ፡፡

ጆ.ስ.ት.፣ ማቴዎስ ፪፡፲፩፡፡ ከማቴዎስ ፪፡፲፩ ጋር አነጻፅሩ

ኢየሱስ መጥምቁ ዮሐንስን ለማገልገል መላእክት ላከ፡፡

፲፩ አሁንም ኢየሱስ ዮሐንስ ወደ እስር ቤት እንደተጣለ አወቀ፣ እና እርሱም መላእክትን ላከ፣ እና እነሆ፣ እነርሱም መጡና አገለገሉት፡፡

ጆ.ስ.ት.፣ ማቴዎስ ፪፡፲፰፡፡ ከማቴዎስ ፪፡፲፱ ጋር አነጻፅሩ

ብሉይ ኪዳን ነብያት ስለኢየሱስ ይናገራሉ፡፡

፲፰ እርሱም በነብያት የተጻፈለት እኔ ነኝ፣ በኋላዬ ኑና ሰዎችን አጥማጆች እን ድትሆኑ አደርጋችኋለሁ አላቸው፡፡

ጆ.ስ.ት.፣ ማቴዎስ ፪፡፳፪፡፡ ከማቴዎስ ፪፡፳ ጋር አነጻፅሩ

ኢየሱስ በስሙ ካመኑት መካከል ህዝቦችን ፈወሰ፡፡

፳፪ ኢየሱስም በምኩራቦቻቸው እያ ስተማረ የመንግሥትንም ወንጌል እየሰ በከ በስሙ በሚያምኑት ሕዝብም መካከል ያለውን ደዌና ሕማም ሁሉ እየፈወሰ በገሊላ ሁሉ ይዞር ነበር፡፡

ጆ.ስ.ት.፣ ማቴዎስ ፳፡፳፪፡፡ ማቴዎስ ፳፡፲፱ ጋር አነጻፅሩ

ትእዛዛትን የሚጠብቁ እና እንደዚህ እንዲያደርጉ የሚ ያስተምሩ ሌሎች ይድናሉ፡፡

፳፪ እንግዲህ ከነዚህ ከሁሉ ካነሱት ትእ ዛዛት አንዲቱን የሚሽር፣ እና ሰዎች እንዲህ እንዲያደርጉ የሚያስተምር፣ ለሰውም እን ዲሁ የሚያስተምር ማንም ሰው በመንግ ሥተ ሰማያት አይድንም፤ እነዚህን የህግ ትእዛዛት እስከሚሟሉ ድረስ የሚያደርግ እና የሚያስተምርም ግን እርሱ በመንግሥተ ሰማያት ታላቅ ይባላል እናም ይድናል፡፡

ጆ.ስ.ት.፣ ማቴዎስ ፲፡፲፩፡፡ ከማቴዎስ ፲፡፲ ጋር አነጻፅሩ፤ በሉቃስ ፲፩፡፲ም እንደዚህ አይነት ቅያሬዎች ነበሩ

ጌታ ወደ ፈተና አይመራንም፡፡

፲፩ ከክፉም አድነን እንጂ ወደ ፈተና ለመግባት እንዳንመራ አትፍቀድልን፡፡

ጆ.ስ.ት.፣ ማቴዎስ ፲፡፳፪፡፡ ከማቴዎስ ፲፡፳፪ ጋር አነጻፅሩ

አይኖቻችን ለእግዚአብሔር ክብር የቀኑ ከሆኑ፣ ሰውነ ቶቻችን በሙሉ በብርሀን ይሞላሉ፡፡

፳፪ የሰውነት መብራት ዓይን ናት፤ ዓይንህ እንግዲህ ለእግዚአብሔር ክብር የቀናች ብትሆን፣ ሰውነትህ ሁሉ ብሩህ ይሆናል፡፡

ጆ.ስ.ት.፣ ማቴዎስ ፮፡፳፫–፳፯።
ከማቴዎስ ፮፡፳፫፤ ፲፡፲ ጋር
አነጻፅሩ

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ስለስራቸው አስቸጋሪነት አስጠነቀቃቸው ነገር ግን መንገድን እንደሚያዘጋጅላ ቸው እና የሰማይ አባት እንደሚሰጣቸው ቃል ገባ።

፳፫ እንደገናም እላችኋለሁ፥ ወደ አለም ሂዱ፣ እናም ስለአለም አታስቡ፤ ምክን ያቱም አለም ይጠላችኋል፣ እናም ይሰ ድዳችኋል፣ እናም ከምኩራባችሁ ያስወ ጧችኋል።

፳፬ ይህም ቢሆን፣ ህዝብን በማስተማር ከቤት ወደቤት ትሄዳላችሁ፤ እኔም በፊ ታችሁ እሄዳለሁ።

፳፭ እናም የሰማይ አባትችሁ ለምግብ ምንም የሚያስፈልጋችሁን፣ ምን እንደ ምትበሉ ይሰጣችኋል፤ እና ለመሸፈኛም፣ የምትለብሱትንም።

ጆ.ስ.ት.፣ ማቴዎስ ፮፡፴፡
ከማቴዎስ ፮፡፴፣ ጋር አነጻፅሩ

መጀመሪያ የእግዚአብሔርን መንግስት ለመገንባት መፈለግ ይገባናል።

፴ ስለዚህ፣ የዚህን አለም ነገሮች አት ፈልጉ ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብ ሔርን መንግሥት ለመገንባት፣ እና ጽድቁ ንም ለመመስረት ፈልጉ፣ እና እነዚህ ነገ ሮች ሁሉ ይጨመርላችኋል።

ጆ.ስ.ት.፣ ማቴዎስ ፯፡፩–፪።
ከማቴዎስ ፯፡፩–፪ ጋር አነጻፅሩ

ፃድቅ ባለመሆን አትፍረዱ።

፩ አሁን እነዚህ ኢየሱስ ደቀ መዛሙ ርቱ ለህዝቦቹ እንዲሏቸው ያስተማራቸው ቃላቶች ናቸው።

፪ እንዳይፈረድባችሁ ፃድቅ ባለመሆን አትፍረዱ፤ ጻድቅ በሆነ ፍርድ ፍረዱ።

ጆ.ስ.ት.፣ ማቴዎስ ፯፡፬–፰።
ከማቴዎስ ፯፡፫–፭ ጋር አነጻፅሩ

ኢየሱስ ደቀመዛሙርቶቹን ከጸሀፊዎች እና ፈሪሳውያ ንን፣ ካህናትን፣ እና ሌዋውያንን በግብዝነታቸው ምክ ንያት እንዲጋጠሟቸው አስተማራቸው።

፬ እናም እንደገና፣ እንዲህ ትሏቸዋላ ችሁ፣ በወንድምህም ዓይን ያለውን ጉድፍ ስለምን ታያለህ፥ በዓይንህ ግን ያለውን ምሰሶ ስለ ምን አትመለከትም?

፭ ወይም ወንድምህን፣ ከዓይንህ ጉድፍ ላውጣ ፍቀድልኝ እንዴትስ ትለዋለህ፤ እና በዓይንህ ምሰሶ እንዳለ አታይምን?

፮ እናም ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ እን ዲህ አለ፣ ጸሀፊዎችን እና ፈሪሳውያንን፣ ካህናትን፣ እና ሌዋውያንን ትመልከታ ችኋልን? በምኩራባቸው ያስተምራሉ፣ ነገር ግን ህግን፣ ትእዛዛትን አይጠብቁም፤ እናም ሁሉም ከመንገዱ ወጥተዋል እናም በኃጢያት ስር ናቸው።

፯ ሂዱ እናም እንዲህ በሏቸው፣ እናንተ ራሳችሁ የብክለት ልጆች ሆናችሁ ሰዎ ችን ህግን እና ትእዛዛትን ለምን ታስተ ምሯላችሁ?

፰ እንዲህም በሏቸው፣ አንተ ግብዝ፥ አስቀድመህ ከዓይንህ ምሰሶውን አውጣ፥ ከዚያም በኋላ ከወንድምህ ዓይን ጉድፉን ታወጣ ዘንድ አጥርተህ ታያለህ።

ጆ.ስ.ት.፣ ማቴዎስ ፯፡፱–፲፩።
ከማቴዎስ ፯፡፯ ጋር አነጻፅሩ

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ንስሀን እንዲሰብኩ እና የመ ንግስትን ሚስጥሮች ከአለም ጋር እንዳይካፈሉ አስ ተማረ።

፱ ንስሀ ግቡ መንግስተ ሰማያት ወደ እናንተ ቀርባለችና ንስሃ ግቡ በማለት ወደ አለም ሂዱ።

፲ እና የመንግስት ሚስጥሮች በውስጣ ችሁ አስቀሩ፤ ምክንያቱ ይህን በእግራቸው እንዳይረግጡት፤ የተቀደሰውን ለውሾች ለመስጠት ብቁ አይደለም፣ ወይም ዕን ቁዎቻችሁንም በእሪያዎች ፊት አትጣሉ።

፲፩ አለም እናንተ እራሳችሁ ልትሸከ ሙት የማትችሉትን ሊቀበሉት አይችሉ ምና፤ ስለዚህ ዕንቁዎቻችሁን አትስጧ ቸው፣ አለበለዚያም ዞረውባችሁ ያጠቋ ችኋል።

ጆ.ስ.ት.፣ ማቴዎስ ፯፡፲፪–፲፯።
ከማቴዎስ ፯፡፣፯–፳ ጋር አነጻፅሩ

ኢየሱስ ለሚጠይቁት ሁሉ አብ ራዕይ እንደሚሰጥ ለደ ቀመዛሙርቶቹ አስተምሩ።

፲፪ እንዲህም በሏቸው፣ እግዚአብ ሔርን ጠይቁ፤ ለምኑ፥ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ፥ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያን አን ኳኩ፥ ይከፈትላችሁማል።

፲፫ የሚለምነው ሁሉ ይቀበላልና፥ የሚ ፈልገውም ያገኛል፥ መዝጊያንም ለሚያ ንኳኳ ይከፈትለታል።

፲፬ ከዚያም ደቀ መዛሙርቶቹ እንዲህ አሉት፣ እንዲህ ይሉናል፣ እኛ ራሳችን ጻድቅ ነን፣ እናም ማንም ሰው እንዲያስ ተምረን አያስፈልገንም። እግዚአብሔር ሙሴን እና አንዳንድ ነቢያትን እንደሰማ እናውቃለን፤ እኛን ግን አይሰማም።

፲፭ እናም እንዲህ ይሉናል፣ ለደህንነ ታችን ህጉ አለን፣ እናም ያም ለእኛ ብቁ ነው።

፲፮ ከዚያም ኢየሱስ መለሰ፣ እናም ለደቀ መዛሙርቱ አለ፣ እንደዚህ ለእነ ርሱ ትመልሳላችሁ፣

፲፯ በእናንተ መካከል፣ ልጅ እያላችሁ፣ እናም እርሱ ተነስቶ፣ አባ፣ እንድገባ እና ከአንተ ጋር እንድመገብ ቤትህን ክፈት ሲል፣ ልጄ ሆይ፣ ግባ፤ የእኔ የሆነ ሁሉ የአንተ ነው፣ እና የአንተም የእኔ ነው የማ ይል ሰው ማን ነው?

ጆ.ስ.ት.፣ ማቴዎስ ፱፡፲፰–፳፭።
ከማቴዎስ ፱፡፲፯–፲፯ ጋር አነጻፅሩ

ኢየሱስ የፈሪሳውያንን ጥምቀት አስወገደ፤ ይህም ምንም ዋጋ የለውም ምክንያቱም እነርሱ እርሱን አይ ቀበሉትምና። እርሱ የሙሴ ህግን የሰጠ እንደሆነ አወጀ።

፲፰ ከእዚያም ፈሪሳዊያን አሉት፣ ህጉን በሙላት እንደምንጠብቅ እያየህ፣ በጥም ቀታችን ለምን አትቀበለንም?

፲፱ ነገር ግን ኢየሱስ አላቸው፣ ህግን አትጠብቁም። ህግን የምትጠብቁ ከሆ ናችሁ፣ ትቀበሉኝ ነበር፣ እኔ ህግን የሰ ጠሁት ነኝና።

፳ በጥምቀታችሁ አልቀበላችሁም፣ ምክንያቱም ምንም አይጠቅማችሁምና።

፳፩ አዲስ የሆነው ሲመጣ፣ የድሮው ለመውጣት የተዘጋጀ ነውና።

ጆ.ስ.ት.፣ ማቴዎስ ፲፩፡፲፫–፲፭።
ከማቴዎስ ፲፩፡፲–፲፩፣ ፲፫–፲፬ ጋር
አነጻፅሩ

መጥምቁ ዮሐንስ ለአዳኝ መንገድን ለማዘጋጀት የሚ መጣው ኢሊያ ነው።

፲፫ ነገር ግን ረባሾች ሀይል የማይኖራ ቸው ቀናት ይመጣሉ፤ ነቢያት ሁሉና ሕጉ እንደተነበዩት እስከ ዮሐንስ ድረስ እንዲህ ይሆናል።

፲፬ አዎን፣ የተነበዩት ሁሉ ስለእነዚህ ቀናት አስቀድመው ተናግረዋል።

፲፭ ይህን ከተቀበላችሁ፣ በእውነትም፣ ሁሉንም ነገሮች የሚያዘጋጅ እና ሁል ዘንድ ያለው ኤልያስ ይህ ነበር።

ጆ.ስ.ት.፣ ማቴዎስ ፲፪፡፴፪–
፴፰። ከማቴዎስ ፲፪፡፴፫–፴፱ ጋር
አነጻፅሩ፤ ደግሞም ጆ.ስ.ት.፣ ሉቃስ
፲፪፡፱–፲፪ ተመልከቱ

በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚናገር አይሰረይለትም።

፴፪ ከዚያም ከጸሀፊዎች አንዳ ንድ መጡ እና ለእርሱም እንዲህ አሉ፣ መምህር፣ እያንዳንዱ ኃጢያት ይሰረያሉ ተብሎ ተፅፏል፤ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚናገር አይሰረይለትም ብለሀል። እናም እንዲህ በማለት ጠየቁ፣ እነዚህ ነገ ሮች እንዴት ይሆናሉ?

፴፫ እርሱም እንዲህ አላቸው፣ ርኩስ መንፈስ ግን ከሰው በወጣ ጊዜ፥ ዕረፍት እየ ፈለገ ውኃ በሌለበት ቦታ ያልፋል፥ አያገኝ ምም፤ ነገር ግን ሰው በመንፈስ ቅዱስ ላይ ሲናገር፣ በዚያን ጊዜም፣ ወደ ወጣሁበት ቤቴ እመለሳለሁ ይላል፤ ቢመጣም ባዶ ሆኖ ተጠርጎና አጊጦ ያገኘዋል፤ ምክንያቱም መልካሙ መንፈስ ለራሱ ይተወዋል።

ጆ.ስ.ት.፣ ማቴዎስ ፲፫፡፡ ፴፱–
፴፭። ከማቴዎስ ፲፫፡፡ ፴፱–፴፪ ጋር
አነጻፅሩ፤ ደግሞም ት. እና ቃ.
፹፯፡፡ ፩–፯ ተመልከቱ

ከአለም መጨረሻ (ከክፉዎች መደምሰስ) በፊት፣ ከሰ ማይ የተላኩ መልእክተኞች ጻድቅን ከክፉዎች መካ ከል ይሰበስባሉ።

፴፱ መከሩም የዓለም መጨረሻ፣ ወይም የክፉዎች መደምሰስ ነው።

፴ አጫጆችም መላእክት፣ ወይም የሰ ማይ መልእክተኞች ናቸው።

፴፩ እንግዲህ እንክርዳድ ተለቅሞ በእሳት እንደሚቃጠል፥ በዓለም መጨረሻ፣ ወይም በክፉዎች መደምሰስ እንዲሁ ይሆናል።

፴፪ ምክንያቱም የሰው ልጅ ከመምጣጡ ከዚያ ቀን በፊት፣ መላእክቱን እና የሰማይ መልእክተኞቹን ይልካል።

፴፫ ከመንግሥቱም እንቅፋትን ሁሉ ዓመፃንም የሚያደርጉትን ይለቅማሉ፣ በክፉዎች መካከልም ይጥሉአቸዋል፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨትም ይሆናል።

፴፬ ምክንያቱም አለም በአቶነ እሳት ትነዳለችና።

ጆ.ስ.ት.፣ ማቴዎስ ፲፮፡፡ ፳፭–፳፱።
ከማቴዎስ ፲፮፡፡ ፳፬–፳፮ ጋር አነጻፅሩ

ኢየሱስ "የአንድን መስቀል ማንሳት" የሚለው ትር ጉም ምን እንደሆነ ገለጸ፥ ጎጥያተኝነትን እና የአለም ስግብግብነትን መካድ እና የእርሱንም ትእዛዛት መጠ በቅ ናቸው።

፳፭ ከእዚያም ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አለ፣ ማንም ሰው ወደ እኔ ከመጣ፣ እራሱን ይርሳ፣ እና መስቀሉን ያንሳና ይከ ተለኝ።

፳፮ አሁን ሰው መስቀሉን ለማንሳት ሁሉንም ኃጢአተኝነትንና እያንዳንዱን ዓለማዊን ምኞት መካድ፣ እና ትእዛዛቴን መጠበቅ ማለት ነው።

፳፯ ነፍሳችን ለማዳን ብላችሁ ትእዛ ዛቴን አተተላለፉ፤ በዚህች አለም ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ በሚመጣው አለም ያጠፋታል።

፳፰ ስለ እኔ ግን በዚህች አለም ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ በሚመጣው አለም ያገ ኛታል።

፳፱ ስለዚህ አለምን ቱ፣ እና ነፍሳችሁን አድኑ፤ ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍ ሱንም ቢያጐድል ምን ይጠቅመዋል? ወይስ ሰው ስለ ነፍሱ ቤዛ ምን ይሰጣል?

ጆ.ስ.ት.፣ ማቴዎስ ፲፯፡፡ ፲–፲፩።
ከማቴዎስ ፲፯፡፡ ፲፩–፲፫ ጋር አነጻፅሩ

ኢየሱስ አንዱ ለማዘጋጀት እና አንዱ ዳግም ለመመ ለስ፣ ስለሚያደርጉት ሁለት ኤልያሶች አስተማረ።

፲ ኢየሱስም መለሰ እና እንዲህ አላቸው፣ ኤልያስማ አስቀድሞ ይመጣል፣ እና በነብ ያት እንደተጻፈው ሁሉንም ነገሮች ደግሞ ይመልሳል።

፲፩ እንደገናም እላችኋለሁ፣ እነሆ፣ መልእክተኛዬን እልካለሁ፣ እና እርሱም መንገዴን በፊቴ ያዘጋጃል ተብሎ ስለእ ርሱ የተጻፈበት ኤልያስ ከዚህ በፊት መጥ ቷል፤ የወደዱትንም ሁሉ አደረጉበት እንጂ አላወቁትም።

፲፪ እንዲሁም ደግሞ የሰው ልጅ ከእነ ርሱ መከራ ይቀበላል።

፲፫ ነገር ግን እላችኋለሁ፣ ኤልያስ ማን ነው? እነሆ፣ መንገዴን በፊቴ እንዲያዘ ጋጅ የላኩት፣ ይህም ኤልያስ ነው።

፲፬ በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ስለ መጥምቁ ዮሐንስ፣ እና ደግሞም በነቢ ያት እንደተጻፈው መጥቶ ሁሉንም ነገ ሮች ዳግም ስለሚመልሰው እንደ ነገራ ቸው አስተዋሉ።

ጆ.ስ.ት.፣ ማቴዎስ ፲፰፡፡ ፲፭። ማቴዎስ
፲፰፡፡ ፲፭ ጋር አነጻፅሩ፤ ደግሞም
ሞሮኒ ፰ ተመልከቱ

ህጻናት ንስሀ መግባት አያስፈልጋቸውም።

፲፭ የሰው ልጅ የጠፋውን ለማዳን፣ እና ጎጥያተኞችን ንስሀ እንዲገቡ ለመጥራት መጥቶአልና፤ ነገር ግን እነዚህ ልጆች ንስሀ መግባት አያስፈልጋቸውም፣ እና እኔም አድናቸዋለሁ።

ጆ.ስ.ት.፣ ማቴዎስ ፲፱፡፲፫።
ከማቴዎስ ፲፱፡፲፫ ጋር አነጻፅሩ

ህጻናት ይድናሉ።

፲፫ በዚያን ጊዜ እጁን እንዲጭንባቸውና እንዲጸልይ ሕፃናትን ወደ እርሱ አመጡ። ደቀ መዛሙርቱም እንዲህ በማለት ገሠጹ አቸው፣ አያስፈልግም፣ ምክንያቱም ኢየሱስ እነዚህ ይድናሉ ብሎአልና።

ጆ.ስ.ት.፣ ማቴዎስ ፳፭፡፴፫።
ከማቴዎስ ፳፭፡፴፪–፴፫ ጋር አነጻፅሩ

ሰው በኢየሱስ ከማመኑ በፊት ንስሀ መግባት አለበት።

፴፫ ዮሐንስ እኔን በሚመለከት ያለውን የማያምን ንስሀ ካልገባ በስተቀር አያም ነኝም።

ጆ.ስ.ት.፣ ማቴዎስ ፳፭፡፴፯–፴፱። ከማቴዎስ ፳፭፡፴፮–፴፱ ጋር አነጻፅሩ

ኢየሱስ ዋና የማዕዘኑም ድንጋይ እንደሆነ ገለጸ። ወን ጌሉ ለአይሁድ ይቀርባል፣ ከዚያም ለአህዛብ። ክፉዎች ኢየሱስ ሲመለስ ይደመሰሳሉ።

፴፯ እና ካህናት እና ፈሪሳዊያን የእርሱን ምሳሌዎች ሲሰሙ፣ ስለእነርሱ እንደተና ገረ ገባቸው።

፴፰ እና እንዲህ ተባባሉ፣ ይህን ታላቅ መንግስት እርሱ ብቻውን አበላሻለሁ ብሎ ያስባል? እና በእርሱም ተናደው ነበር።

፴፱ ነገር ግን ሊይዙትም ሲፈልጉት ሳሉ ሕዝቡ ፈሩአቸው፣ ምክንያቱም ህዝቡ እንደ ነቢይ እንደሚያዩት ስላወቁ።

፴ አሁንም ደቀመዛሙርቱ ወደ እርሱ መጡ፣ እና ኢየሱስ አላቸው፣ ለእነርሱ በተናገርኩት የምሳሌ ቃሎቼ ተደንቃች ኋል?

፴፩ እውነት እላችኋለሁ፣ እኔ አለት ነኝ፣ እና ክፉዎቼ ተቃወሙኝ።

፴፪ የማዕዘን ራስ ነኝ። እነዚህ አይሁዶች ይወድቁብኛል፣ እና ይሰበራሉ።

፴፫ የእግዚአብሔር መንግሥት ከእነርሱ ትወሰዳለች፣ ፍሬዋንም ለሚያመጣ ሕዝብ ትሰጣለች፤ (ይህም ማለት አህዛቦች)።

፴፬ ስለዚህ፣ ድንጋዩ የሚወድቅበት ይፈጨዋል።

፴፭ እና የወይኑ አትክልት ጌታ በሚ መጣ ጊዜ፣ እነርሱ የማይረቡ ክፉ ሰዎ ችን ያጠፋቸዋል፣ እና የወይኑንም አት ክልት ስፍራውን፣ እንዲሁም በመጨረ ሻው ቀናት ፍሬውን በየጊዜው ለሚያስ ረክቡ ለሌሎች ገበሬዎች ይሰጠዋል።

፴፮ ከእዚያም ጌታ ከሰማይ ምድር ወደ ሆነው ወደ ወይን አትክልቱ እና በእርሷ ውስጥ ወደሚኖሩት ሲወርድ፣ አህዛቦ ችም ደግመው እንደሚጠፉ የነገራቸው ምሳሌ ገባቸው።

ጆ.ስ.ት.፣ ማቴዎስ ፳፫፡፲። ከማቴዎስ ፳፫፡፱ ጋር አነጻፅሩ

በሰማይ ያለው ፈጣሪያችን ነው።

፲ ማንንም በምድር ላይ ፈጠሪያችሁ፣ ወይም የሰማይ አባታችሁ ብላችሁ አት ጥሩ፤ አንዱ እርሱም፣ እንዲሁም በሰማይ ውስጥ ያለው፣ የሰማይ አባታችሁና ፈጣ ሪያችሁ ነውና።

ጆ.ስ.ት.፣ ማቴዎስ ፳፭፲፤ ፳፭፲፣ ፳፭፲–፳፭፲፰። ከማቴዎስ ፳፭፲፤ ፳፭፲–፳፭፲፤ ከጆ.ስ.ት.፣ ማርቆስ ፲፬፡፳–፳፭ ጋር አነጻፅሩ

ኢየሱስ መጀመሪያ የቅዱስ ቁርባንን እንጀራ ቆረሰ እናም ባረከው። ቅዱስ ቁርባን የኢየሱስ ስጋ እና ደም መታሰቢያ ነው።

፳፭ ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ ቆርሶም ባረከ፣ እናም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና አላቸው፣ እንካችሁ፣ ብሉ፣ ይህ ለእ ናንተ በቤዛነት የሰጠሁትን ሥጋዬ ለማስ ታወስ ነው።

፳፮ ይህም በስሜ ለሚያምኑት ሁሉ ለኃ ጢአታቸው ስርየት የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜን ለማስታወስ ነው።

፳፯ እና ትእዛዝም እሰጣችኋለሁ፣ እኔ ሳደርግ ያያችሁትን ነገሮች በትጋት አድ ርጉ፣ እና እስከመጨረሻም ስለእኔ መስ ክሩ።

ጆ.ስ.ት.፣ ማቴዎስ ፳፯፡፫–፮።
ከማቴዎስ ፳፯፡፫–፭፤ ከሐዋርያት
ስራ ፩፡፲፤ ጋር አነጻፅሩ

የይሁዳ ሞት ተገልጿል።

፫ በዚያን ጊዜ አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ
እንደ ተፈረደበት አይቶ ተጸጸተ፣ እና
ሠላሳውንም ብር ለካህናት አለቆችና ለሽ
ማግሎች መልሶ፣

፬ ንጹሕ ደም አሳልፌ በመስጠቴ በድያ
ለሁ አለ።

፭ እነርሱ ግን ለእርሱ እንዲህ አሉት፣
እኛስ ምን አግዶን? አንተው ተጠንቀቅ፤
ኃጢያትህም በራስህ ላይ ይሁን።

፮ እና ብሩንም በቤተ መቅደስ ጣለ፣ እና
ሄደና እራሱን በዛፍ ላይ አነቀ። ወዲያውም
ወደቀ፣ እና ከመካከሉ ተሰነጠቀ አንጀ
ቱም ሁሉ ተዘረገፈ፣ ሞተም።

ጆ.ስ.ት.፣ ማርቆስ ፪፡፳፯–፳፯።
ከማርቆስ ፪፡፳፯–፳፰ ጋር አነጻፅሩ

የሰው ልጅ የሰንበት ጌታ ነው ምክንያቱም ሰንበትን
ሰርቷታልና።

፳፯ ስለዚህ ሰንበት ለሰው የተሰጠችው
ለእረፍት፤ እና ደግሞም ሰው እግዚአብ
ሔርን ያክብር ዘንድ፣ እንጂ እንዳይበላም
አይደለም፤

፳፰ ሰንበት በሰው ልጅ ተፈጥሮአል፣
እንዲሁም የሰው ልጅ ለሰንበት እንኳ ጌታዋ
ነው።

ጆ.ስ.ት.፣ ማርቆስ ፫፡፳፭–፳፭።
ከማርቆስ ፫፡፳፫–፳ ጋር አነጻፅሩ

በመንፈስ ቅዱስ ላይ ከሚሳደቡት በስተቀር፣ ኢየሱስ
ንስሀ የሚገቡ ኃጢያተኞችን በሙሉ ይሰርይላቸዋል።

፳፭ አንዳንዶችም ወደ እርሱ መጡ፣
እንዲህ በማለትም ከሰሱት፣ ራስህን የእ
ግዚአብሔር ልጅ በማድረግ ለምን ኃጢ
ያተኞችን ትቀበላለህ።

፳፮ ነገር ግን እርሱም መለሳቸው እናም
እንዲህ አለ፣ እውነት እላችኋለሁ፥ ሰዎች
ለሚሰሩት ኃጢአት ሁሉ፣ ንስሀ ሲገቡ፣
ይሰረይላቸዋል፤ ለሰው ልጆች ንስሀ ለመ
ስበክ መጥቻለሁና።

፳፫ የሚሳደቡትም ስድብ ሁሉ፣ ወደ
እኔ ለሚመጡት፣ እና እኔ ሳደርግ ያዩ
ትን ለሚያደርጉ ይሰረይላቸዋል።

፳፬ ነገር ግን የማይሰረይለት አንድ
ኃጢያት አለ። በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚ
ሳደብ ግን ለዘላለም አይሰረይለትም፤ ነገር
ግን ከአለም ለመቆረጥ በአደጋ ላይ ነው
የሚገኘው። እናም የዘላለም ፍርድን ይወ
ርሳሉና።

፳፭ እርሱም እንዲህ ያላቸው እነርሱ
ርኵስ መንፈስ አለበት ስለሚሉ ነበርና።

ጆ.ስ.ት.፣ ማርቆስ ፯፡፲–፲፪።
ከማርቆስ ፯፡፲ ጋር አነጻፅሩ

ኢየሱስ ነቢያትን የሚያስወግዱ እና የሙሴን ህግ የማ
ያከብሩን ወቀሰ።

፲ ባስወገዳችኋቸው ነቢያት ስለእናንተ
በሙላት ይህም ተጽፏል።

፲፩ ስለእነዚህ ነገሮችም በእውነት መስ
ክረዋል፣ እናም ደማቸውም በእናንተ ላይ
ይሆናል።

፲፪ የእግዚአብሔርን ስርዓቶች አል
ጠበቃችሁም፤ ሙሴ፣ አባትህንና እናት
ህን አክብር፤ ደግሞ አባቱን ወይም እናቱን
የሰደበ፣ በህጋችሁ ውስጥ እንደተፃፈው
የተላላፊ ሞት ፈጽሞ ይሙት ብሎአልና፤
ግን ህግን አታከብሩም።

ጆ.ስ.ት.፣ ማርቆስ ፰፡፴–፴፰።
ከማርቆስ ፰፡፴ ጋር አነጻፅሩ

ስለኢየሱስ ለመሞት ፈቃደኛ የሆነ ደህንነትን ይቀበ
ላል።

፴፯ ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠ
ፋታልና፤ ወይም ነፍሱን ሊያድን የሚ
ወድ፣ ስለእኔ ይህችን አሳልፎ ለመስጠት
ፈቃደኛ ይሆናል፤ እናም ስለእኔ አሳልፎ
ለመስጠት ፈቃደኛ ያለሆነ፣ እርሱም ያጠ
ፋታል።

፴፰ ስለ እኔና ስለ ወንጌል ነፍሱን ለማ
ጥፋት ፈቃደኛ የሆነ ሁሉ ግን ያድናታል።

ጆ.ስ.ት.፣ ማርቆስ ፰፡፴፪–፴፫። ከማርቆስ ፰፡፴ ጋር አነጻፅሩ

በክርስቶስ የሚያፍሩት በመጀመሪያው ትንሳኤ ምንም ክፍል የላቸውም፣ ስለክርስቶስ ለመሞት ፈቃደኛ የሆኑት ግን ከእርሱ ጋር በክብሩ ይመጣሉ።

፴፪ ሲመጣም በዚያ ትንሳኤ ክፍል አይኖራቸውም።

፴፫ በእውነት እላችኋለሁ፣ እርሱም ይመጣል፤ እና ስለእኔ እና ስለወንጌል ህይወትን የሚሰጥ፣ ከእርሱ ጋር ይመጣል፣ እናም በሰው ልጅ ቀኝ በኩልም በዳመና ውስጥም በክብሩ ይለበሳል።

ጆ.ስ.ት.፣ ማርቆስ ፱፡፫። ከማርቆስ ፱፡፬ ጋር አነጻፅሩ

መጥምቁ ዮሐንስ በመለወጫ ተራራ ላይ ነው።

፫ እና ኤልያስ ከሙሴም ጋር ታዩአቸው፣ ወይም በሌላ ቃላት፣ መጥምቁ ዮሐንስ እና ሙሴ፤ እና ከኢየሱስም ጋር ይነጋገሩ ነበር።

ጆ.ስ.ት.፣ ማርቆስ ፱፡፴–፴፰። ከማርቆስ ፱፡፴–፴፰ ጋር አነጻፅሩ

ኢየሱስ የሚያሰናክል እጅን ወይም እግርን መቁረጥ ወደ ተሳሳተው መንገድ ከሚመራ ሰው ጓደኝነት ማስ ወገድ ጋር አነጻፅሯል።

፴ ስለዚህ፣ እጅህ ብታሰናክልህ ቍረጣት፤ ወይም ወንድምህ ካሰናከለህ እና ካልተናዘዘ እና ካልተወው፣ እርሱም ይቆረጣል። ሁለት እጅ ኖሮህ ወደ ገሃነም ከመሄድ ጉንድሽ ሆነህ ወደ ሕይወት መግባት ይሻላል።

፴፩ አንተ እና ወንድምህ ትላቸው ወደ ማይሞትበት እሳቱም ወደማይጠፋበት ወደ ገሃነም ወደማይጠፋ እሳት ከመሄዳችሁ፣ አንተ ወደ ህይወት ካለወንድምህ መግባት ይሻላልና።

፴፪ እንደገናም፣ እግርህ ብታሰናክልህ ቍረጣት፤ መሰረትህ የሆነው፣ የምትራመድበት፣ ተላላፊ ከሆነ፣ እርሱም ይቆረጣል።

፴፫ ሁለት እግር ኖሮህ እሳቱም ወደማይጠፋበት ወደ ገሃነም ከመጣል አንካሳ ሆነህ ወደ ሕይወት መግባት ይሻልሃል።

፴፬ ስለዚህ እያንዳንዱም ሰው ለሌላ፣ ወይም ሌላን በማመን ሳይሆን፣ ለእራሱ ይቁም ወይም ይውደቅ።

፴፭ አባቴን ጠይቁ፣ እና እንደምትቀበሉ እምነት ኖሮአችሁ፣ በእምነት ከጠየቃችሁ በምትጠይቁበት ወዲያው ይደረግላችኋል።

፴፮ የሚያይላችሁ አይናችሁ፣ ብርሀን እንዲያሳያችሁ እንዲጠብቃችሁ የተመደበላችሁ፣ ተላላፊ ሆኖ ካሰናከላችሁ፣ አውጡት።

፴፯ ሁለት አይኖች ኖሮህ ወደ ገሃነም እሳት ከመጣል በአንድ አይን ወደ እግዚአብሔር መንግስት መግባት ይሻልሃል።

፴፰ አንተ ከወንድምህ ጋር ትላቸው ወደማይሞትበት እሳቱም ወደማይጠፋበት ወደ ገሃነም ከመሄዳችሁ፣ አንተ ብትድን ይሻላልና።

ጆ.ስ.ት.፣ ማርቆስ ፲፪፡፲፱። ከማርቆስ ፲፪፡፲፩ ጋር አነጻፅሩ

እግዚአብሔር የሙታን አምላክ አይደለም፣ ምክንያቱም ሙታንን ከመቃብራቸው ያስነሳልና።

፲፱ ስለዚህ የሕያዋን አምላክ ነው እንጂ የሙታን አይደለም፤ ከመቃብራቸው ያስነሳቸዋልና። እንግዲህ እጅግ ትስታላችሁ።

ጆ.ስ.ት.፣ ማርቆስ ፲፫፡፳–፳፮። ከማርቆስ ፲፫፡፲፱–፳፭ ጋር አነጻፅሩ

ኢየሱስ ቅዱስ ቁርባንን ለእርሱ ስጋ እና ደም መታሰቢያነት መሰረተ።

፳ ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ ባረከ ቆርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና አላቸው፣ እንካችሁ፣ ብሉ።

፳፩ እነሆ፣ ይህም ሰውነቴን ለማስታወስ ነው፤ ይህን በየጊዜው ስታደርጉም ከእናንተ ጋር የነበርኩበትን ሰአት ታስታውሳላችሁና።

፳፪ ጽዋንም አንሥቶ፣ እና ካመሰገነ በኋላ ሰጣቸው፤ ሁሉም ከእርሱ ጠጡ።

፲፯፤ እና እንዲህም አላቸው፣ ይህም ለብዙዎች የሚፈስ፣ እና የምስጣችሁ የአዲስ ኪዳን ደሜን ለማስታወስ ነው፤ ስለእኔ ለአለም ሁሉ ምስክር ትሰጣላችሁና።

፲፰ ይህን ስነስራአት በየጊዜው ስታደርጉም፣ ከእናንተ ጋር የነበርኩበትን እና ከጸዋው ከእናንተ ጋር የጠጣሁበትን፣ እንዲሁም የአግልግሎቴ የመጨረሻ ጊዜን፣ ይህን ሰአት ታስታውሳላችሁ።

፲፱ እውነት እላችኋለሁ፣ ስለዚህ ምስክር ስጡ፣ በእግዚአብሔር መንግሥት ከወይኑ ፍሬ አዲሱን እስከምጠጣበት እስከዚያ ቀን ድረስ ከእናንተ ጋር ደግሞ አልጠጣ ውምና።

፲፭ እና አሁን እነርሱም አዝነው ነበር፣ በእርሱም ላይ አለቀሱ።

ጆ.ስ.ት.፣ ማርቆስ ፲፪፡፲፭–፴፰።

ከማርቆስ ፲፪፡፴–፴፪ ጋር አነጻፅሩ

በጌቴሴማኒ፣ አስራ ሁለቱም ቢሆኑ የኢየሱስን መሲህነት ሚና ሙሉ በሙሉ አልተረዱትም።

፴፮ ጌቴሴማኒ ወደምትባልም ቦታ መጡ፣ ይህም አትክልት ስፍራ ነበር፤ እና ደቀመዝሙርቱ መደነቅ ጀመሩ፣ እና በጣምም ተጨነቁ፣ እና ይህ መሲህ እንደሆነ እያሰቡ በልቦቻቸውም ቅሬታ ተሰማቸው።

፴፯ እና ኢየሱስ ልቦቻቸውን በማወቅ ደቀ መዝሙርቱንም፣ ስጸልይ ሳለሁ፣ በዚህ ተቀመጡ አላቸው።

፴፰ ጴጥሮስንና ያዕቆብን ዮሐንስንም ከእርሱ ጋር ወሰደ፤ እና ገሰጻቸው፣ ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ እጅግ አዘነች፤ በዚህ ቆዩ ትጉም አላቸው።

ጆ.ስ.ት.፣ ማርቆስ ፲፮፡፲–፲፮።

ከማርቆስ ፲፮፡፱–፲፤ ሉቃስ ፳፬፡፪–፱ ጋር አነጻፅሩ

ሁለት መላእክቶች ሴቶችን በአዳኝ መቃብር አጠገብ ሰላም አሏቸው።

፲ ነገር ግን ሲመለከቱ፣ ድንጋዩ ተንከባሎ እንደ ነበር ተመለከቱ (ይህም እጅግ ትልቅ ነበርና፣) እና ነጭ ልብስ የተጎናጸፉ ሁለት መላእክቶች በዚህ ላይ ተቀምጠው አዩና ደነገጡ።

፱ ነገር ግን መላእክቶቹ አትደንግጡ አሉአቸው፤ የተሰቀለውን የናዝሬቱን ኢየሱስን ትፈልጋላችሁ፤ ተነሥቶአል፥ በዚህ የለም፤ እነሆ እርሱን ያኖሩበት ስፍራ።

፲ እና ሄዳችሁ ለደቀ መዝሙርቱ ለጴጥሮስም ወደ ገሊላ ይቀድማችኋል፤ እንደ ነገራችሁ በዚያ ታዩታላችሁ ብላችሁ ንገሩ አቸው።

፲፩ እና እነርሱ ወደመቃብር ውስጥ በመግባት ኢየሱስን ያኖሩበትን ስፍራ ተመለከቱ።

ጆ.ስ.ት.፣ ሉቃስ ፩፡፲፯። ከሉቃስ ፩፡፲

ጋር አነጻፅሩ

የመጥምቁ ዮሐንስ አባት ዘካሪያስ የክህነት ሀላፊነቱን አከናወነ።

፲ እርሱም በክህነት ስልጣኑ ስነ ስርዓት ውስጥ የክህነት ሀላፊነቱን በእግዚአብሔር ፊት ሲያገለግል፣

ጆ.ስ.ት.፣ ሉቃስ ፪፡፳፤። ከሉቃስ

፪፡፳፤ ጋር አነጻፅሩ

በቤተመቅደስ ውስጥ መምህራን ኢየሱስን አዳመጡ እና ጥያቄዎችንም ጠየቁት።

፳፤ እና እንዲህም ሆኖ አለፈ፣ ከሦስት ቀንም በኋላ በመምህራን መካከል ተቀምጦ በመቅደስ አገኙት፣ እና እነርሱ ይሰሙት፣ እና ጥያቄዎች እርሱን ይጠይቁት ነበር።

ጆ.ስ.ት.፣ ሉቃስ ፫፡፩–፲፭። ከሉቃስ

፫፡፩–፲ ጋር አነጻፅሩ

ክርስቶስ እንደተተነበየው ደህንነትን ለእስራኤል እና ለአህዛብ ለማምጣት ይመጣል። በዘመን ፍጻሜ፣ በአለም ላይ ለመፍረድ እንደገና ይመጣል።

፩ በነቢዩ በኢሳይያስ ቃል መጽሐፍ ውስጥ እንደተጻፈው፤ እና ቃላቶቹም እነዚህ ናቸው፣ የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥር ጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረበዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ አለ።

፲ እነሆ፣ እና አስተውሉ፣ በነቢያት

መፅሀፍ ውስጥ እንደተጻፈውም የአለምን ጎጥያቶች ለማሰወገድና ወደ አህዛብ ህዝቦችም ደህናነትን ለማምጣት፣ የጠፉት ንም፣ የእስራኤል በግ መንጋዎች የሆኑ ትን፣ ለመሰብሰብ ይመጣል።

፲ አዎን፣ እንድሁም የተበተኑትን እና የሚሰቃዩትን፤ ደግሞም መንገድን ለማ ዘጋጀት፣ እና ለአህዛባት ወንጌልን ለመ ስበክ የሚቻልም ለማድረግ፤

፲፩ በጭለማ ጥላ ተቀምጠው ላሉትም፣ እስከ ምድር ዳርም ድረስ፣ ብርሀን ለመ ሆን፤ የሙታንን ትንሳኤ ለማምጣት፣ እና በአብ ቀኝ እጅ በኩል ለመኖር ወደላይም ለማረግ፣

፲፪ እስከ ዘመን ፍጻሜ፣ እና ህግ እና ምስክር እስከሚታተም፣ እና የመንግስት ቁልፍም ወደ አብ እስከሚመለሱ ድረስ፤

፲፫ ለሁሉም ፍርድ ለመስጠት፤ በሁሉም ላይ ለፍርድ ለመውረድ፣ እና እግዚአብ ሔርን የማያመልኩ ሰዎች ስለሰሩት እግዚ አብሔርን የማያመልኩ ስራቸውን እንዲ ያውቁ ለማድረግ፤ እና ይህም ሁሉ በሚ መጣበት ቀን።

፲፬ ይህም የሀይል ቀን ነውና፣ አዎን፣ እንዲሁም እያንዳንዱ ዐዘቅቱ ሁሉ ይሞ ላል፣ እና እያንዳንዱ ተራራውና ኮረብታ ውም ሁሉ ዝቅ ይላል፤ ጠማማውም የቀና መንገድ ይሆናል፣ ሸካራውም መንገድ ትክ ክል ይሆናልና፤

፲፭ ሥጋም የለበሰ ሁሉ የእግዚአብሔ ርን ማዳን ያያል።

ጆ.ስ.ት.፣ ሉቃስ ፮፡ ፲፬–፳፡ ከሉቃስ ፮፡ ፲–፲፮ ጋር አነጻፅሩ

ደሆች ከግምጃ ቤት ትርፍራፊ እንክብካቤ ያገኛሉ። ቀራጮችም በህግ ከተመደበላቸው በላይ ምንም አይ ወስዱም።

፲፬ ቴዎፍሎስ፣ ይህም በአንተ በደንብ ይታወቃል፣ በአይሁዳ ልምድ መሰረት፣ እና ገንዘብን ወደ ግምጃ ቤት በሚቀበሉ በት በህጋቸው ባህል መሰረት፣ ከተቀበ ሉት ግምጃ ቤት ትርፍ ውስጥ ለድሆች ተመድቧል፣ ለእያንዳንዱ ሰው ክፍሉም፤

፲፭ እና ከዚህም መንገድ ቀራጮችም አደረጉ፣ ስለዚህ ዮሐንስ ከታዘዘላችሁ አብልጣችሁ አትውሰዱ አላቸው።

ጆ.ስ.ት.፣ ሉቃስ ፮፡ ፳፭–፴፡ ከሉቃስ ፮፡ ፳–፳፩ ጋር አነጻፅሩ

ኢየሱስ ከጠላት ጋር ከመከራከር በመሰደድ መጽናት ይሻላል ብሎ አስተማረ።

፳፭ ጉንጭህን ለሚመታህ ደግሞ ሁለተ ኛውን ስጠው፡ ወይም፣ በሌላ ቃል፣ እን ደገና ከመሳደብ ሌላውን መስጠት ይሻ ላል። ጐናጸፊያህንም ለሚወስድ እጀ ጠባ ብህን ደግሞ አትከልክለው።

፴ ጠላትህ እነዚህ ነገሮች እንዲወስድ መፍቀድ፣ ከእርሱ ጋር ከመጣላት ይሻ ላልና። በእውነት እላችኋለሁ፣ በሚስጥር የሚያየው የሰማይ አባታችሁ ያን ክፉውን ወደ ፍርድ ያመጣልና።

ጆ.ስ.ት.፣ ሉቃስ ፱፡ ፳፭–፳፮። ከሉቃስ ፱፡ ፳፭–፳፮ ጋር አነጻፅሩ

የአለም ሀብትን ማግኘት የራስን ነፍስ ከማጣት የሚጠ ቅም አይደለም።

፳፮ ነፍሱን ሊያድን የሚወድ፣ ይህችን ለእኔ ለማጣት ፈቃደኛ መሆን አለበት፤ እና ስለ እኔ ነፍሱን ለማጣት ፈቃደኛ የሆነ ግን ያድናታል።

፳፯ ሰው ዓለሙን ሁሉ አትርፎ፣ ግን እግዚአብሔር የሾመውን ካልተቀበለ፣ እና ነፍሱን ቢያጠፋ፣ እና እርሱ ራሱ ንም ቢያጐድል ምን ይጠቅመዋል?

ጆ.ስ.ት.፣ ሉቃስ ፲፭፡ ፱፲። ከሉቃስ ፲፭፡ ፱፪ ጋር አነጻፅሩ

የቅዱስ መጻሕፍት ሙሉነት የእውቀት ቁልፍ ነው።

፱፲ እናንተ ሕግ አዋቂዎች ወዮላችሁ! የእውቀትን መክፈቻ፣ የቅዱስ መጻሕፍት ሙሉነትን ወሰዳችኋልና፤ ራሳችሁ ወደ መንግስት አልገባችሁም፤ እና የሚገቡት ንም ከለከላችሁ።

ጆ.ስ.ት.፣ ሉቃስ ፲፤፡፣ ፱–፲፤፡። ከሉቃስ ፲፤፡፣ ፱–፲ ጋር አነጻፅሩ፤ ደግሞም ጆ.ስ.ት.፣ ማቴዎስ ፲፤፡፣ ፴፯–፴፰ እና ት. እና ቃ. ፲፴፤፡፣ ፰፯–፰፯ ተመልከቱ

ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስን መስደብ እንደማይሰረይ ገለጸ።

፱ ነገር ግን እኔን በሰው ፊት የሚክደኝ፣ በእግዚአብሔር መላእክቶች ፊት ይካዳል።

፲ አሁን ደቀ መዛሙርቱ ይህን ያለው ስለእርሱ በሰዎች ፊት ክፉን ተናግረው ስለነበር እንደሆነ አወቁ፤ በሰዎች በፊት ስለእርሱ ለመመስከር ፈርተው ነበርና።

፲፩ እና እንዲህ በማለትም እርስ በራሳቸው እየተወያዩ አሉ፣ ልባችንን ያው ቃል፣ እና ለኩነኔአችን ይናገራል፣ እና አይሰረይልንም። ነገር ግን እርሱ መለሳቸው፣ እና እንዲህም አላቸው፣

፲፪ በሰው ልጅም ላይ ቃል የሚናገር፣ እና ንስሀ የሚገባ፣ ሁሉ ይሰረይለታል፤ መንፈስ ቅዱስን የሚሰድብ ግን አይሰረይ ለትም።

ጆ.ስ.ት.፣ ሉቃስ ፲፤፡፣ ፴፩–፴፯። ከሉቃስ ፲፤፡፣ ፴፯–፴፰ ጋር አነጻፅሩ

ኢየሱስ አገልጋዮቹ ለእርሱ መምጣት ሁልጊዜም መዘጋጀት እንዳለባቸው ገለጸ።

፴፩ እነሆ በለሊቱ በመጀመሪያ ክፍል ይመጣልና፣ እና በሁተኛው ክፍልም ደግሞ ይመጣል፣ እና እንደገናም በሶስ ተኛው ክፍልም ይመጣል።

፴፪ እና እውነት እላችኋለሁ፣ ስለእርሱ እንደተጻፈውም አስቀድሞም መጥቷል፤ እንደገናም ከሌሊቱም በሁለተኛው ወይም በሦስተኛው ክፍል መጥቶ እንዲሁ ቢያገ ኛቸው፣ እነዚያ ባሪያዎች ብፁዓን ናቸው፤

፴፫ የእነዚያ አገልጋዮች ጌታ ይታጠ ቃል፣ እና ምግብ ለመመገብም ይቀመ ጣሉ፣ እና መጥቶም ያገለግላቸዋል።

፴፬ አሁንም፣ የጌታ መምጣት እንደሌባ በማታ እንደሚመጣ እነዚህን ነገሮች እን ድታውቁ ዘንድ፣ እውነት እላችኋለሁ።

፴፭ እና ይህም እቃዎቹን ካልጠበቀ በማያውቅበት ሰአት ሌባ እንደመጣበት እና እቃዎቹን እንደወሰደበት እና ከጓደ ኞቹ ጋር እንደተከፋፈለበት ባለቤት ሰው አይነት ነው።

፴፮ እና እርስ በራሳቸውም ተባባሉ፣ ጥሩው ባለቤት በምን ሰዓት ሌባ እንዲመጣ ቢያውቅ ኖሮ፣ በነቃ፣ ቤቱም እንዲቆፈር ባልፈቀደም፣ እና እቃዎቹን ባላጣ ነበር።

፴፯ እና እንዲህ አላቸው፣ እውነት እላችኋለሁ፣ እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታ ችሁ ኑሩ፤ የሰው ልጅ በማታስቡበት ሰዓት ይመጣልና።

፴፰ ጴጥሮስም ጌታ ሆይ፣ ይህን ምሳሌ ለእኛ ወይስ ደግሞ ለሁሉ ትናገራለህን? አለው።

፴፱ ጌታም አለ፣ የተናገርኩት እንኪ ያስ ምግባቸውን በጊዜው ለልጆቹ ለሚ ሰጧቸው ጌታ በቤተ ሰዎቹ ላይ ለሚሾ ሙት ነው።

፵ እነርሱም ታማኝና መጋቢ አገልጋይ ማን ነው? አሉ።

፵፩ ጌታም አላቸው፣ ይህም የምግቡን ክፍል በጊዜው ለመስጠት የሚጠብቀው አገልጋይ ነው።

፵፪ ጌታው መጥቶ እንዲህ ሲያደርግ የሚያገኘው ያ ባሪያ ብፁዕ ነው።

፵፫ እውነት እላችኋለሁ፣ ባለው ሁሉ ላይ መሪ ያደርገዋል።

፵፬ ያ ክፉ ባሪያ ግን ሲጠብቅ የማይገ ኘው ነው። እና ያ ባሪያ ሳይጠብቅ ከተ ገኘ፣ በልቡም ጌታዬ እስኪመጣ ይዘገያል ብሎ ያስባል፤ እና ሎሌዎችን ባሪያዎችና ገረዶችንም መምታት፣ መብበምላትም፣ መጠጣትም፣ መስከርም ይጀምራል።

፵፭ የዚያ ባሪያ ጌታ ባልጠበቃት ቀን ባላ ወቃትም ሰዓት ይመጣል፣ ከሁለትም ይሰ ነጥቀዋል እድሉንም ከማይታመኑ ጋር ያደ ርጋል።

፵፮ የጌታውንም ፈቃድ አውቆ፣ ለጌ ታው መምጣት ያልተዘጋጀ እንደ ፈቃዱም ያላደረገ ያ ባሪያ እጅግ ይገረፋል።

፲፯ የጌታውን ፈቃድ ያላወቀ፣ መገረፍ የሚገባውንም ያደረገ ግን ጥቂት ይገረፋል። ብዙም ከተሰጠው ሰው ሁሉ ከእርሱ ብዙ ይፈለግበታል፤ ጌታ ብዙ አደራም ከተሰጠው ከእርሱ ሰዎች አብዝተው ይሹበታል።

ጆ.ስ.ት.፣ ሉቃስ ፲፪፡፴፭–፴፮።
ከሉቃስ ፲፪፡፴፭ ጋር አነጻፅሩ

ሙሴን እና ነቢያትን የሚያውቁ በኢየሱስ ያምናሉ።

፴፭ ከእነርሱ አንዳንዶቹ ወደ እርሱ መጡ፣ መምህር፣ ሙሴ እና ነቢያት አሉን፣ እናም በእነርሱ የሚኖር ሁሉ፣ ህይወት አይኖረውምን? አሉ።

፴፮ እና ኢየሱስ መልሶ አለ፣ ሙሴን ወይም ነቢያትን አታውቁም፤ የምያውቋቸው ቢሆን ኖሮ፣ በእኔ ታምኑ ነበርና፤ ለዚህ ምክንያት ነበር የተጻፉትና። እኔ የተላኩት እናንተ ህይወት ይኖራችሁ ዘንድ ነው። ስለዚህ መልካም ከሆ ነው ጨው ጋር አመሳስለዋለሁ፤

፴፯ ጨው አልጫ ቢሆን ግን በምን ይጣፈጣል?

ጆ.ስ.ት.፣ ሉቃስ ፲፮፡፲፮–፳፫።
ከሉቃስ ፲፮፡፲፮–፲፰ ጋር አነጻፅሩ

ህግ እና ነቢያት ስለኢየሱስ ይመሰክራሉ። ፈሪሳውያን መንግስትን ለመደምሰስ ይፈልጋሉ። ኢየሱስ የሀብታሙን ሰው እና የአልዓዛርን ምሳሌ አስተዋወቀ።

፲፮ እንዲህም አሉት፣ ህግና ነቢያት አለን፤ ነገር ግን ይህን ሰው አለቃችን እንዲሆን አንቀበለውም፤ እራሱን በእኛ ላይ ዳኛ ያደርጋልና።

፲፯ ከዚያም ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፣ ህግ እና ነቢያት ስለእኔ ይመሰክራሉ፤ አዎን፣ እና የጻፉት ነቢያት ሁሉ፣ እንዲሁም ዮሐንስ፣ ስለእነዚህ ቀናት ቀድመው ተናግረዋል።

፲፰ ከዚያ ጀምሮ የእግዚአብሔር መንግሥት ይሰበካል፤ እውነትን የሚፈልግ ሁሉም ወደ እርስዋ በኃይል ይገቡባታል።

፲፱ እና ከሕግ አንዲት ነጥብ ከምትወድቅ ሰማይና ምድር ሊያልፍ ይቀላል።

፳ እና ለምን ህግን እያስተማራችሁ የተጻፈውን ትክዳላችሁ፤ እና እንድት ድኑ ዘንድ ህግን ለማሟላት አብ የላከውን ታኮንናላችሁ?

፳፩ እናንተ ደንቆሮዎች! በልባችሁ እግዚአብሔር የለም ብላችኋለን። እና የቀናውን መንገድም አጣማችኋል፤ እና በእናንተም መንግሥተ ሰማያት ትገፋለች፤ እና ትሁቶችን አሳዳችኋል፤ እና በሁከታችሁም መንግስትን ለመደምሰስ ትፈልጋላችሁ፤ እና የመንግስት ልጆችንም በግድ ትወስዳላችሁ። ለእናንተ ዘማዊዎችም ወዮላችሁ!

፳፪ ዘማዊ ናቸው ስላለም በእርሱ ተናድደው እንደገናም ሰደቡት።

፳፫ ነገር ግን ቀጥሎም አለ፣ ሚስቱንም የሚፈታ ሁሉ ሌላይቱንም የሚያገባ ያመነዝራል፤ ከባልዋም የተፈታችውን የሚያገባ ያመነዝራል። እውነትም እላችኋለሁ፣ እናንተን እንደ ሀብታሙ ሰው አመሳስላችኋለሁ።

ጆ.ስ.ት.፣ ሉቃስ ፲፯፡፳፭። ከሉቃስ ፲፯፡፳–፳፭ ጋር አነጻፅሩ

የእግዚአብሔር መንግስት አስቀድማ መጥታለች።

፳፭ ደግሞም እንኋት በዚህ ወይም እንኋት በዚያ አይሉአትም፣ እነሆ የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችሁ ናትና አላቸው።

ጆ.ስ.ት.፣ ሉቃስ ፲፯፡፴፮–፴፯።
ከሉቃስ ፲፯፡፴፮ ጋር አነጻፅሩ

ኢየሱስ ስለኋለኛው ቀናት መሰብሰብ ለመግለጽ የንስርን ምሳሌ ተናገረ።

፴፮ መልሰውም ጌታ ሆይ፣ ወዴት ይወሰዱ? አሉት።

፴፯ እርሱም ሥጋ ወዳለበት፣ ወይም በሌላ ቃላቶች፣ የትም ቅዱሳን በተሰበሰቡበት፣ በዚያ አሞራዎች ይሰበሰባሉ፣ ወይም በዚያ የሚቀሩትም አብረው ይሰበሰባሉ አላቸው።

፴፰ ይህን የተናገረው የቅዱሳንን መሰ

ብሰብ በሚመለከት ነው፤ እና መላእክ
ቶች ወርደው የሚቀሩትን ስለመሰብሰባ
ቸው ነው፤ አንዱን ከመኝታ፣ ሌላን ከወ
ፍጮ፣ እና ሌላን ከሜዳ፣ የትም ከሚፈ
ልግበት።

፴፬ በእውነትም ጻድቅ የሚኖርበት
አዲስ ሰማያትና አዲስ ምድር ይኖራሉ።

፴፭ እና ምንም እርኩስ ነገር አይገኝበ
ትም፤ ምድርም አሮጌ፣ እንዲሁም እንደ
ልብስ፣ ሆና ብከላም ተጨምሮባታልና፣
ይህም ቢሆን ይህም ይጠፋል፣ እና የእ
ግር መርገጫም፣ ከጎጥያት ጻድታ፣ በቅ
ድስና ትቀራለች።

ጆ.ስ.ት.፣ ሉቃስ ፲፰፡፳፯፲፮። ከሉቃስ ፲፰፡፳፯፲፮ ጋር አነጻፅሩ

በባለጠግነት ማመን ወደ እግዚአብሔር መንግስት
መግባትን ይከለክላል።

፳፯፲፮ እርሱ በሀብቶች ለሚያምኑት ወደ
እግዚአብሔር መንግስት ለመግባት አስቸ
ጋሪ ነው፤ ነገር ግን የዚህ አለም የሆኑትን
ነገሮች የተወውም፣ በእግዚአብሔር ዘንድ
ይቻላል፣ ለመግባትም ይችላል አላቸው።

ጆ.ስ.ት.፣ ሉቃስ ፳፩፡፳፰–፳፱። ከሉቃስ ፳፩፡፳፰–፳፱ ጋር አነጻፅሩ

ኢየሱስ ስለመምጫው አንዳንድ ምልክቶች ተናገረ።

፳፰ አሁን ስለ ኢየሩሳሌም መጥፋትን
በሚመለከት እነዚህን ነገሮች ተናገራ
ቸው። ከእዚያም ደቀ መዛሙርቱ እንዲህ
ብለው ጠየቁት፣ መምህር፣ ስለመመለ
ስህ ንገረን?

፳፱ እርሱም መልሶ አላቸው፣ የአ
ሕዛብም ዘመን በሚፈጸምበት የትውልድ
ዘመን በፀሐይና በጨረቃም በከዋክብትም
ምልክት ይሆናል፤ በምድር ላይም አሕዛብ
ከባሕሩና ከሞገዱም ድምፅ የተነሣ እያመ
ነቱ ይጨነቃሉ። ምድር እና የታላቅ ባህር
ውሀዎች ደግመውም ይጨነቃሉ።

፳፯ የሰዎች ልቦችም ስለፈሩ እና ወደ
ምድር የሚመጡትን ነገሮች ስለሚመለ
ከቱ ወደቁባቸው። የሰማይ ሀይላትም ይን
ቀጠቀጣሉ።

ጆ.ስ.ት.፣ ሉቃስ ፳፭፡፴፪። ከሉቃስ ፳፭፡፴፪ ጋር አነጻፅሩ

የአህዛብ ዘመን ሲሟላ ሁሉም ነገሮች ይሟላሉ።

፴፪ እውነት እላችኋለሁ፣ የአህዛብ ዘመን
የሚሟላበት ጊዜ ትውልድ፣ ሁሉም እስ
ኪሟላ ድረስ ይህ ትውልድ አያልፍም።

ጆ.ስ.ት.፣ ሉቃስ ፳፫፡፴፭። ከሉቃስ ፳፫፡፴፭ ጋር አነጻፅሩ

ኢየሱስ እየሰቀሉት ላሉ የሮሜ ወታደሮች ይቅርታ
ጠየቀ።

፴፭ ኢየሱስም አባት ሆይ፣ የሚያደርጉ
ትን አያውቁምና ይቅር በላቸው አለ (ይህም
ማለት የሰቀሉትን ወታደሮች) እና ልብሱ
ንም ተካፍለው ዕጣ ተጣጣሉ።

ጆ.ስ.ት.፣ ሉቃስ ፳፬፡፪–፬። ከሉቃስ ፳፬፡፪–፬ ጋር አነጻፅሩ

ሴቷ በኢየሱስ መቃብር አጠገብ ሁለት መላእክት
አየች።

፪ ድንጋዩንም ከመቃብሩ ተንከባሎ
እናም ሁለት መላእክትም የሚያንጸባርቅ
ልብስ ለብሰው በአጠገቡ ቆመው አገኙት።

፫ እናም ወደ መቃብሩ ገብተውም የጌ
ታን የኢየሱስን ሥጋ ባለማግኘታቸው፣
እነርሱም በዚህ አመነቱ፤

፬ ፈርተውም ፊታቸውን ወደ ምድር
አቀረቀሩ። ነገር ግን እነሆ መላእክት እን
ዲህ አሉአቸው። ሕያውን ከሙታን መካ
ከል ስለ ምን ትፈልጋላችሁ?

ጆ.ስ.ት.፣ ዮሐንስ ፮፡፮–፴፬። ከዮሐንስ ፮፡፮–፴፬ ጋር አነጻፅሩ

የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ከመጀመሪያው ጊዜ ጀምሮ
ተሰብኳል። መጥመቁ ዮሐንስ የክርስቶስን መንገድ
የሚያዘጋጀው ኤልያስ ነው፣ እና ኢየሱስ ክርስቶ
ስም ሁሉንም ነገሮች ደግሞ የሚመልሰው ሌላው ኤል
ያስ ነው።

፮ በመጀመሪያው ወንጌሉ በወልድ
በኩል ተሰብኮ ነበር። እና ወንጌሉም ቃል

ነበረ፣ ቃልም በወልድ ዘንድ ነበረ፣ ወል
ድም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር፣ ወል
ድም ከእግዚአብሔር ነበረ።

፪ ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር
ዘንድ ነበረ።

፫ ሁሉም ነገሮች በእርሱ ተሰርተው
ነበር፤ እና ከተሰራውም አንዳች ስንኳ ያለ
እርሱ አልተሰራም።

፬ በእርሱ ወንጌል ነበረች፣ እና ወንጌ
ልም ሕይወት ነበረች፣ ሕይወትም የሰዎች
ብርሃን ነበረች።

፭ ብርሃንም በአለም ይበራል፣ አለምም
አላስተዋለውም።

፮ ከእግዚአብሔር የተላከ ስሙ ዮሐንስ
የሚባል አንድ ሰው ነበረ።

፯ ስለ ብርሃን ይመሰክር ዘንድ፣ በወ
ልድ በኩል ስለወንጌሉ ለሁሉም ይመ
ሰክር ዘንድ፣ በእርሱ በኩል ሰዎች ያምኑ
ዘንድ፣ ይህ ለምስክር ወደ አለም መጣ።

፰ ስለ ብርሃን ሊመሰክር መጣ እንጂ፣
እርሱ ያ ብርሃን አልነበረም፣

፱ ወደ ዓለም ለሚመጣው ሰው ሁሉ የሚ
ያበራው እውነተኛው ብርሃን ነበር፤

፲ እንዲሁም የእግዚአብሔር ልጅ እን
ዲህ ነው። በዓለም የነበረው፣ ዓለሙም በእ
ርሱ ሆነ፣ ዓለሙም አላወቀውም።

፲፩ የእርሱ ወደ ሆነው መጣ፥ የገዛ ወገኖ
ቹም አልተቀበሉትም።

፲፪ ለተቀበሉት ሁሉ ግን፣ በስሙ ለሚ
ያምኑት ብቻ፣ ለእነርሱ የእግዚአብሔር
ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው።

፲፫ እርሱም ከእግዚአብሔር ተወለደ
እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም
ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም።

፲፬ ያም ቃል ሥጋ ሆነ፣ በእኛም አደረ፣
ክብሩንም እንደ አብ አንድያ ልጅ ክብር፣
ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ፣ አየን።

፲፭ ዮሐንስ ስለ እርሱ መሰከረ እንዲህም
ብሎ ጮኸ፣ ስለ እርሱ ያልሁት ይህ ነበረ፣
ከእኔ በኋላ የሚመጣው፣ ከእኔ ይልቅ የከ
በረ ሆኖአል፤ እርሱ ከእኔ በፊት ነበረና።

፲፮ በመጀመሪያም ቃል ነበረ፣ እንዲ
ሁም በስጋ የነበረውና በአብ ፈቃድ መሰ
ረት የተላከልን ወልድ። እና በስሙ ያመ
ኑት ሁሉ ሙሉነቱን ተቀበሉ። እና በጸጋው
በኩልም፣ ከሙላቱም፣ እንዲሁም የማይ
ጠፋ ህይወት እና የዘለአለማዊ ህይወት፣
ሁላችንም ተቀብለናል።

፲፯ ሕግ በሙሴ ተሰጥቶ ነበርና፣ ህይ
ወት እና እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ
በኩል መጣ።

፲፰ ምትን የሚያመጣ የሥጋ ትእዛዝ
ሕግ አይነት ነበርና፤ ወንጌል ግን የአብ
እቅፍ በሆነው በአንድያ ልጅ ኢየሱስ ክር
ስቶስ በኩል መጨረሻ የሌለው ህይወት
ሀይል እንዳለው አይነት ነው።

፲፱ እናም ስለወልድ ምስክርን ካልመ
ሰከረ በስተቀር፣ መቼም ቢሆን እግዚአብ
ሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም፤ በእርሱ
ካልሆነ በስተቀር ማንም ሰው አይድንም።

፳ ይህም የዮሐንስ ምስክር ነው፣ ከኢ
የሩሳሌም አይሁዶች ቄሶች እና ሌዊ ወደ
እርሱ ልከው ጠየቁት፤ አንት ማን ነህ?

፳፩ ኤልያስ እንደሆነ መሰከረም አል
ካደምም፤ ነገር ግን እኔ ክርስቶስ አይደለ
ሁም ብሎ መሰከረ።

፳፪ እነርሱም እንኪያስ ኤልያስ ነህ?
ብለው ጠየቁት። እርሱም ሁሉንም ነገሮች
ደግሞ የሚመልሰው ያ ኤልያስ አይደለ
ሁም አለ። እነርሱም ነቢዩ ነህን? ብለው
ጠየቁት። አይደለሁም ብሎ መለሰ።

፳፫ እንኪያስ ማን ነህ? ለላኩን መልስ
እንድንሰጥ፤ ስለራስህ ምን ትላለህ? አሉት።

፳፬ እርሱም ነቢዩ ኢሳይያስ እንዳለ የጌ
ታን መንገድ አቅኑ ብሎ በምድረበዳ የሚ
ጮኽ ሰው ድምፅ እኔ ነኝ አለ።

፳፭ የተላኩትም ከፈሪሳውያን ነበሩ።

፳፮ እንኪያስ አንተ ክርስቶስ ወይም
ሁሉን ነገሮች ደግሞ የሚመልሰው ኤል
ያስ ወይም ነቢዩ ካይደለህ ስለ ምን ታጠም
ቃለህ? ብለው ጠየቁት፣ አሉትም።

፳፯ ዮሐንስ መልሶ፣ እኔ በውኃ አጠም
ቃለሁ፤ ዳሩ ግን እናንተ የማታውቁት በመ
ካከላችሁ ቆሞአል አላቸው፤

፳፯ እርሱም የምመሰክርለት ነው። እር ሱም እኔ የጫማውን ጠፍር ልፈታ የማይገ ባኝ፣ ወይም በታውን ለመሙላት የማል ችል፣ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔ ይልቅ የሚከብር ነቢይ፣ እንዲሁም ኤልያስ፣ ይህ ነው፤ እርሱም በውሀ ብቻ ሳይሆን፣ በእሳ ትና በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃል አላቸው።

፳፰ በነገው ዮሐንስ ኢየሱስን ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ እንዲህ አለ፤ እነሆ የዓለምን ኃጢያት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ!

፳፱ ዮሐንስም ለህዝቦች ስለእርሱ እንዲህ ሲል መሰከረ፣ አንድ ሰው ከእኔ በኋላ ይመ ጣል፣ ከእኔ ይልቅ የከበረ ሆኖአል ከእኔም በፊት ነበርና፣ አውቀውም ነበር፣ እና እር ሱም ለእስራኤል ይታያል፣ ስለዚህ በውሀ ለማጥመቅ መጣሁ ብዬ ስለ እርሱ ያልሁት ይህ ነው።

፴፩ ዮሐንስም እንዲህ ብሎ መሰከረ፤ በእኔ ሲጠመቅ፣ መንፈስ ከሰማይ እንደ ርግብ ሆኖ ሲወርድ አየሁ፤ በእርሱ ላይም ኖረ።

፴፪ እኔም አውቀው ነበር፤ በውኃ አጠ ምቅ ዘንድ የላከኝ እርሱ ነውና፤ መንፈስ ሲወርድበትና ሲኖርበት የምታየው፣ በመ ንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ እርሱ ነው አለኝ።

፴፫ እኔም አይቻለሁ እርሱም የእግዚአ ብሔር ልጅ እንደ ሆነ መስክሬአለሁ።

፴፬ እነዚህም ነገሮች ዮሐንስ ያጠምቅ በት በነበረው በዮርዳኖስ ማዶ በቤተ ራባ ሆነ።

ጆ.ስ.ት.፣ ዮሐንስ ፤ ፣ ፴፪። ከዮሐንስ ፤ ፣ ፴፪ ጋር አነጻፅሩ

ኬፋ "ባለራዕይ" ወይም "አለት" ማለት ነው

፴፪ ወደ ኢየሱስም አመጣው። ኢየሱስም ተመልክቶ፣ አንተ የዮና ልጅ ስምዖን ነህ፣ አንተ ኬፋ ትባላለህ አለው፤ ትርጓሜው ባለራዕይ ወይም አለት ማለት ነው። እነ ርሱም አሳ አጥማጆች ነበሩ። እነርሱም ወዲያው ሁሉንም ተው፣ እና ኢየሱስን ተከተሉ።

ጆ.ስ.ት.፣ ዮሐንስ ፤ ፣ ፤–፤። ከዮሐንስ ፤ ፣ ፤–፤ ጋር አነጻፅሩ

ፈሪሳውያን ኢየሱስን ለመግደል ፈለጉ። እርሱም ጥቂት ጥምቀቶችን አከናወነ፣ ነገር ግን ደቀ መዛሙ ርቱ ተጨማሪዎችን አከናወኑ።

፤ እንግዲህ። ኢየሱስ ከዮሐንስ ይልቅ ደቀ መዛሙርት ያደርጋል ያጠምቅማል ማለትን ፈሪሳውያን እንደ ሰሙ፣

፣ በትጋት ሊገድሉት የሚፈልጉበት መንገድ ፈለጉ፤ ብዙዎች ዮሐንስን እንደ ነቢይ ተቀብለውት ነበርና፣ ነገር ግን በኢ የሱስ አላመኑም።

፣ ምንም እንኳን እርሱ ከደቀመዛሙርቱ እንዳጠመቁት ያህል ባያጠምቅም፣ አሁን ጌታ ይህን አውቋል፤

፤ እርስ በርሳቸው እንደሚከባበሩ ምሳሌ ለማሳየት ፈቀደላቸው።

ጆ.ስ.ት.፣ ዮሐንስ ፤ ፣ ፳፤። ከዮሐንስ ፤ ፣ ፳፤ ጋር አነጻፅሩ

እግዚአብሔር መንፈሱን በእውነት ለሚያምኑት ቃል ገባ።

፳፤ ለእነዚህ አይነትም እግዚአብሔር መንፈሱን ቃል ገብቷል። የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈል ጋቸዋል።

ጆ.ስ.ት.፣ ዮሐንስ ፤ ፣ ፳፤። ከዮሐንስ ፤ ፣ ፳፤ ጋር አነጻፅሩ

የአብ ፍላጎት ሁሉም ኢየሱስን እንዲቀበሉ ነው። የኢ የሱስ ፍላጎትን የሚያደርጉ በጻድቃን ትንሳኤ ይነሳሉ።

፳፤ የላከኝ አብ ፈቃድን ከሚያደርገው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም። እናም ይህም የላከኝ ፈቃድ ነው፣ እናንተ ወልድን እንድትቀበሉ፤ አብምስለእርሱ ይመሰክራልና፤ እናም ምስክሩን የሚቀ በል፣ እና የላከኝን ፈቃድ የሚያደርግ፣ እኔም በጻድቃን ትንሳኤ አስነሣዋለሁ።

ጆ.ስ.ት.፣ ዮሐንስ ፤፤፣ ፳–፤።

ከዮሐንስ ፤፤፣ ፳–፤ ጋር አነጻፅሩ

ኢየሱስ የአይሁድ ህግን ለመፈጸም የሐዋሪያትን እግ ሮች አጠበ።

፲ ጴጥሮስም የእኔን እግር ማጠብ አያስ ፈልግህም አለው። ኢየሱስም ካላጠብሁህ፣ ከእኔ ጋር ዕድል የለህም ብሎ መለሰለት።

፱ ስምዖን ጴጥሮስም ጌታ ሆይ፣ እጆቼ ንና ራሴን ደግሞ እንጂ እግሮቼን ብቻ አይ ደለም አለው።

፲ ኢየሱስም እጆንና ራሱን ያጠበ፣ የሚያስፈልገው እግሩን መታጠብ ብቻ ነው፣ ሁለንተናው ግን ንጹሕ ነው፤ እና ንተም ንጹሐን ናችሁ፣ ነገር ግን ሁላችሁ አይደላችሁም አለው። *አሁን ይህ በሀጋ ቸው ውስጥ የአይሁድ ባህል ነበር፤ ይህም ቢሆን ኢየሱስ ይህን ያደረገው ህግ እንዲ ሟላ ነበር።*

ጆ.ስ.ት.፣ ዮሐንስ ፲፭፡፡ ከዮሐንስ ፲፭፡ ፡ ጋር አነጻፅሩ

የጭለማ ልውል፣ ወይም ሰይጣን፣ የዚህ አለም ነው።

ከእንግዲህ ወዲህ ከእናንተ ጋር ብዙ አልናገርም፣ የዚህ ዓለም የሆነው የጭለማ ልዑል ይመጣልና፤ ግን በእኔ ላይም ሀይል የለውም፣ ግን በእናንተ ላይ ሀይል አለው።

ጆ.ስ.ት.፣ የሐዋርያት ስራ ፱፡፲፡ ከየሐዋርያት ስራ ፱፡፲፤ ፲፩፡፡ ፱ ጋር አነጻፅሩ

ጳውሎስ በሚቀየርበት ጊዜ አብረውት የነበሩት ብርሀ ንን አዩ፣ ነገር ግን ድምፅን አልሰሙም ወይም ጌታን አላዩም።

ከእርሱም ጋር በመንገድ የሄዱ ሰዎች በእርግጥም ብርሀንን አዩ፣ ፈሩም፤ እር ሱን የሚያናግረውን ሰው ድምፅን ግን አልሰሙም።

ጆ.ስ.ት.፣ የሐዋርያት ስራ ፲፩፡፡ ፲፩–፲፪። ከየሐዋርያት ስራ ፲፩፡፡ ፲፩–፲፪ ጋር አነጻፅሩ

ዋናው ሻለቃ ጳውሎስን ከታሰረበት ፈታው።

፲፩ ስለዚህም ሊመረምሩት ያሰቡት ከእ ርሱ ወዲያው ተለዩ፤ የሻለቃውም ደግሞ ሮማዊ መሆኑን ባወቀ ጊዜ ፈራ፣ አሳስሮት ነበርና፣ እናም ከታሰረበት ፈታው።

፲፪ በማግሥቱም አይሁድ የከሰሱት በምን ምክንያት እንደ ሆነ እርግጡን ያውቅ ስለነ በር፣ እርሱም የካህናት አለቆችና ሽንጎውም ሁሉ ይሰበሰቡ ዘንድ አዘዘ፥ ጳውሎስንም አውርዶ በፊታቸው አቆመው።

ጆ.ስ.ት.፣ ሮሜ ፫፡፡ ፭–፰። ከሮሜ ፫፡ ፡ ፭–፰ ጋር አነጻፅሩ

ሰው መልካም ነገርን ለማምጣት ክፉ ማድረግ እንደማ ይችል ጳውሎስ አስተማረ።

፭ ነገር ግን በዓመፃችን ቀርተን እና የእ ግዚአብሔርን ጽድቅ የምናሞግስ ከሆንን፣ ቍጣን የሚያመጣ እግዚአብሔር ዓመፀኛ ነው ለማለት እንዴት እንደፍራለን? (እግ ዚአብሔርን እንደሚፈራ ሰው እላለሁ፣)

፮ እንዲህ አይሁን፤ እንዲህ ቢሆን እግዚ አብሔር በዓለም እንዴት ይፈርዳል?

፯ በእኔ ውሸት (ይህም በይሁዳዎች እን ደዚህ ነው የሚጠራው) ግን የእግዚአብሔር እውነት ለክብሩ ከላቀ፣ ስለምን በእኔ ደግሞ እንደ ኃጢአተኛ ገና ይፈርድብኛል? እናም አንቀበልም? እንዲሁ ይሰድቡናልና።

፰ አንዳንዱም እንዲሁ እንድንል ይናገ ራሉና፣ (የእነርሱም ፍርድ ቅን ነው) መል ካም እንዲመጣ ክፉ አናደርግም። ግን ይህ ሀሰት ነው።

ጆ.ስ.ት.፣ ሮሜ ፪፡፡ ፪–፭። ከሮሜ ፪፡ ፡ ፪–፭ ጋር አነጻፅሩ

ሰው ለመዳን የሚችለው፣ የሙሴ ህግን ከመከተል ጋር ባለው ስራ ሳይሆን፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ብቻ ነው።

፪ አብርሃም በሥራ ህግ ጻድቆ ቢሆን፣ በራሱ ክብር አለው፤ ግን በእግዚአብሔር ዘንድ አይደለም።

፫ ቅዱስ መጽሐፍስ ምን አለ? አብርሃ ምም እግዚአብሔርን አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት።

፬ በሥራ ህግ ጻድቆ የሆነው ለሚሠራ ደመወዝ እንደ ዕዳ ነው እንጂ እንደ ጸጋ አይቈጠርለትም፤

፭ ነገር ግን በሥራ ህግ ጽድቅ ለመ ሆን ለማይፈልገው፣ ግን ኃጢአተኛው

ንም በማያጸድቀው ለሚያምነው፣ እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቆጠርለታል።

ጆ.ስ.ት.፣ ሮሜ ፬፡፲፤ ከሮሜ ፬፡፲ ጋር አነጻፅሩ

እምነት እና ስራም፣ በጸጋ በኩል፣ ለደህንነት አስፈላጊ ነው።

፲፤ ስለዚህ እስከመጨረሻ ድረስ በእምነት እና በስራ፣ በጸጋ በኩል ቃል ኪዳን እንዲጸና ዘንድ ጸድቃችኋል፤ ይህም በህግ ለሆኑት ብቻ ሳይሆን ደግሞ አባታችን ለሆነው ከአብርሃም እምነት ለሆኑት ለዘሩ ሁሉ ነው።

ጆ.ስ.ት.፣ ሮሜ ፤፡፡–፤፤ ከሮሜ ፤፡–፤፤ ጋር አነጻፅሩ

የሰዎችን ነፍሶች ቋሚ በሆነ ሁኔታ ለመልካም ለመቀየር ሀይል ያለው ክርስቶስ ብቻ ነው።

፤ በህግ መሰረት ያልሆነው፣ በሥጋ ሳለን በሕግ የሚሆን የኃጢአት መሻት ለሞት ፍሬ ሊያፈራ በብልቶቻችን ይሠራ ነበርና።

፤ አሁን ግን ለእርሱ ለታሰርንበት፣ በሀጉ ሞተን፣ ከሕግ ተፈትተናል፥ ስለዚህም በአዲሱ በመንፈስ ኑሮ እንገዛለን እንጂ በአሮጌው በፊደል ኑሮ አይደለም።

፤ እንግዲህ ምን እንላለን? ሕግ ኃጢአት ነውን? ይህ ከእኛ ይራቅ። አይደለም፣ ነገር ግን በሕግ ባይሆን ኃጢአትን ባላወቅሁም ነበር፤ ሕጉ አትመኝ ባላለ ምኞትን ባላወቅሁም ነበርና።

፤ ኃጢአት ግን ምክንያት አግኝቶ ምኞትን ሁሉ በትእዛዝ ሠራብኝ። ኃጢአት ያለ ሕግ ምውት ነውና።

፤ እኔም ዱሮ ሕግ ባለመተላለፍ ሕያው ነበርሁ፣ የክርስቶስ ትእዛዝ በመጣች ጊዜ ግን ኃጢአት ሕያው ሆነ፣ እኔም ሞትሁ።

፤ ለሕይወትም የተሰጠችውን፣ የመጣችውን የክርስቶስ ትእዛዝ ሳላምንም፣ እርስዋን ለሞት ያኮነነችኝ ሆና አገኘኋት።

፤ ኃጢአት ምክንያት አግኝቶ ትእዛዝን በማስወገድ አታሎኛልና፤ በእርስዋም ተገድያለሁ።

፤ ይህም ቢሆን፣ ሕጉ ቅዱስ፣ ትእዛዙም ቅድስትና ጻድቅ በጎም ሆነው አገኘዋቸው።

፤ እንግዲህ በጎ የሆነው ነገር ለእኔ ሞት ሆነብኝን? ይህ ከእኛ ይራቅ። ነገር ግን ኃጢአት፣ ኃጢአትም በትእዛዝ ምክንያት ያለልክ ኃጢአተኛ ይሆን ዘንድ፣ ኃጢአትም እንዲሆን ይገለጥ ዘንድ በጎ በሆነው ነገር ለእኔ ሞትን ይሠራ ነበር።

፤ ትእዛዝ መንፈሳዊ እንደ ሆነ እናውቃለንና፤ እኔ ግን በህግ በታች ስሆን፣ ከኃጢአት የተሸጥሁ የሥጋ ነበርኩኝ።

፤ አሁን ግን መንፈሳዊ ነኝ፤ እንዳደርግ የታዘዝኩትን አደርጋለሁና፤ እና እንዳልፈቅድ የታዘዝኩትን አልፈቅድምና።

፤ ትክክል እንደሆነ የማላውቀውን አላደርግም፤ ጎጥያት የሆነውን እጠላለሁና።

፤ ከእዚያም የማልፈቅደውን አላደርግም፣ ለህግም ጥሩ እንደሆነ እስማማለሁ፤ አልተከነንኩምም።

፤ እንደዚህ ከሆነ ምንም ጎጥያት አልሰራም፤ ነገር ግን በእኔ የሚያድር ኃጢያትን ለመቋቋም እፈልጋለሁ እንጂ።

፤ በእኔ ማለት በሥጋዬ በጎ ነገር እንደማይኖር አውቃለሁና፤ ፈቃድ አለኝና፣ መልካሙን ግን ማድረግን፣ ከክርስቶስ ውስጥ በስተቀር፣ አላገኘሁም።

፤ በህግ ውስጥ እያለሁ መልካም የማደርገው፣ በጎ ሆኖ አላገኘሁትምና፤ ስለዚህ አላደርገውም።

፤ ነገር ግን በህግ ውስጥ የማላደርገውን ክፋት፣ በጎ ሆኖ አግኝቻለሁ፤ ያንንም አደርጋለሁ።

፤ አሁን ያን በክርስቶስ እርዳታ ካደረግኩኝ፣ በህግ ውስጥ አላደርገውም፣ ከህግ በታችም አይደለሁም፤ እናም ምንም ጥፋትን ለመስራት አልፈልግም፣ ነገር ግን በእኔ የሚያድር ኃጢአትን ለመቋቋም እፈልጋለሁ እንጂ።

፳፫ እንግዲያስ በህግ በታች መልካሙን ሳደርግ በእኔ ክፉ እንደሚያድብኝ አግኝ ቻለሁ፤ በውስጡ ሰውነቴ በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለኛልና።

፳፬ አሁንም ሌላ ሕግ አያለሁ፣ እንዲ ሁም የክርስቶስ ትእዛዝ፣ እና በአዕምሮ ሮዬም ታትሟል።

፳፭ ነገር ግን ብልቶቼ ከአእምሮዬ ሕግ ጋር ይዋጋሉ፣ በብልቶቼ ባለ በኃጢአት ሕግ ወደሚማርከኝ ያመጣኛል።

፳፮ እና በውስጤ ያለውን ኀጥያት ካልተቋቋምኩኝ፣ ከስጋ ጋር ግን የኀጥ ያት ህግን አገለግላለሁ፤ እኔ ምንኛ ኀስቃላ ሰው ነኝ! ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?

፳፯ በኢየሱስ ክርስቶስ በጌታችን ለእ ግዚአብሔር ምስጋና እሰጣለሁ፣ እንግዲ ያስ እኔ በአእምሮዬ በእግዚአብሔር ሕግ እገዛለሁ።

፮.ስ.ት.፣ ሮሜ ፰፡፰። ከሮሜ ፰፡፰ ጋር አነጻፅሩ

የስጋ መንገድን የሚከተሉት እግዚአብሔርን አያስደ ስቱም።

፰ በሥጋ ያሉትም እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኙት አይችሉም።

፮.ስ.ት.፣ ሮሜ ፰፡፳፩–፳፡ ከሮሜ ፰፡፳፩–፳ ጋር አነጻፅሩ

ኢየሱስ ክርስቶስ ጻድቅን ለደህንነታቸው ለማዘጋጀት ይቀድሳቸዋል።

፳፩ እርሱም ልጁ በብዙ ወንድሞች መካ ከል በኵር ይሆን ዘንድ፥ አስቀድሞ ያወቃ ቸው፣ የእርሱን መልክ እንዲመስሉ አስቀ ድሞ ደግሞ ወስኖአልና።

፳ አስቀድሞም የወሰነውን እነዚህን ደግሞ ጠራ፤ የጠራውንም እነዚህን ደግሞ አጸደቀው፤ ያጸደቀውንም እነዚህን ደግሞ አከበረ።

፮.ስ.ት.፣ ሮሜ ፲፫፡፮–፯። ከሮሜ ፲፫፡፮–፯ ጋር አነጻፅሩ

ህዝባዊ ባለስልጣኖችን የሚያከብሩ ለእግዚአብሔር ያላቸውን ክብር ከፍተኛ እና በጣው ፍጹም የሆነ ያደ ርጉታል።

፮ ስለዚህ ደግሞ ለእነርሱ ስለታችሁን ትገብራላችሁና፤ በዚህ ነገር የሚተጉ የእ ግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸውና።

፯ ግን በመጀመሪያ፣ ለሁሉ የሚገባ ውን አስረክቡ፤ ግብር ለሚገባው ግብ ርን፣ ቀረጥ ለሚገባው ቀረጥን፣ ስለታች ሁም መፈራት ለሚገባው መፈራትን በማ ድረግ፣ እና ክብር ለሚገባው ክብርን ስጡ።

፮.ስ.ት.፣ ፮ ቆሮንቶስ ፯፡፮–፪፣ ፭፣ ፳፮፣ ፳፱–፴፫፣ ፴፯፡ ከ፮ ቆሮንቶስ ፯፡፮–፪፣ ፭፣ ፳፮፣ ፳፱–፴፫ ጋር አነጻፅሩ

ጳውሎስ ጋብቻ የሚፈለግ እንደሆነ አስተማረ። በሚ ስዮን የተጠሩት፣ ግን፣ በአገልግሎታቸው ጊዜ ያላገቡ ቢሆኑ እግዚአብሔርን በተሻለ ለማገልገል ይችላሉ።

፮ አሁን እናንተ እንዲህ ብላችሁ ስለ ጻፋችሁልኝ ነገሮች በሚመለከት፣ ከሴት ጋር አለመገናኘት ለሰው መልካም ነው።

፪ ነገር ግን ስለ ዝሙት ጠንቅ ለእያንዳ ንዱ ለራሱ ሚስት ትኑረው ለእያንዳንዲቱ ደግሞ ለራስዋ ባል ይኑራት እላችኋለሁ።

፫ ለጸሎት ትተጉ ዘንድ ተስማምታ ችሁ ለጊዜው ካልሆነ በቀር፣ እርስ በርሳ ችሁ አትከላከሉ፤ ራሳችሁን ስለ አለመ ግዛት ሰይጣን እንዳይፈታተናችሁ ደግሞ አብራችሁ ሁኑ።

፴፮ እንግዲህ ስለ አሁኑ ችግር ይህ መል ካም ይመስለኛል፤ ሰው እንዲህ ሆኖ ቢኖር ታላቅ መልካም ያደርጋልና።

፴፱ ነገር ግን ወደአገልግሎት ለተጠራ ችሁት እናገራለሁ። ወንድሞች ሆይ፥ ይህን እናገራለሁ፣ ዘመኑ አጭር ነው፣ ወደ አገ ልግሎት እንድትላኩ ዘንድ። እንዲሁም ሚስቶች ያሉአቸውም እንደሌላቸው ይሆ ናሉ፤ እናንተ ተጠርታችኋል እና የጌታን ስራ ለመስራት ተመርጣችኋልና።

፴ የሚያለቅሱም እንደማያለቅሱ ይሆን ብላቸዋል፤ ደስ የሚላቸውም ደስ እንደማ ይላቸው፣ እና የሚገዙም ምንም እንደሌላ ቸው ይሆንላቸዋል፤

፴፩ በዚችም ዓለም የሚጠቀሙ በሙሉ እንደማይጠቀሙባት ይሆናሉ፤ የዚች ዓለም መልክ አላፊ ነውና።

፴፪ ነገር ግን ወንድሞች ጥሪአችሁን እንድታጎሉ ፍላጎቴ ነው። ያለ አሳብ ልት ኖሩ እወዳለሁ። ያላገባው ጌታን እንዴት ደስ እንዲያሰኘው የጌታን ነገር ያስባልና፤ ስለዚህ ያሸንፋል።

፴፫ ያገባው ግን ሚስቱን እንዴት ደስ እንዲያሰኛት የዓለምን ነገር ያስባል፤ ስለ ዚህ ልዩነት አለ፣ ተደናቅፎአልና።

፴፬ እንዲሁም ያገባ እርሱም መልካም አደረገ፤ ያላገባም እርሱም የተሻለ አደረገ።

ጆ.ስ.ት.፣ ፮ ቆሮንቶስ ፲፭፣፴፡

ከ፮ ቆሮንቶስ ፲፭፣፴ ጋር አነጻፅሩ

በትንሳኤ ሶስት የክብር ደረጃዎች አሉ።

፴ ደግሞ የሰለስቲያል አካሎች፣ የተረ ስትሪያል አካሎች፣ እና የቲለስቲያል አካ ሎች አሉ፤ ነገር ግን የሰለስቲያል ክብር፣ አንድ፤ እና የተረስትሪያል ሌላ፤ እና የቲለ ስቲያል ሌላ ነው።

ጆ.ስ.ት.፣ ፪ ቆሮንቶስ ፭፣፲፮፡

ከ፪ ቆሮንቶስ ፭፣፲፮ ጋር አነጻፅሩ

ጳውሎስ ቅዱሳንን በስጋ አይነት ኑሮ እንዳይኖሩ መከ ራቸው።

፲፮ ስለዚህ እኛ ከአሁን ጀምሮ በምንም በሥጋ አንኖርም፤ አዎን፣ ድሮም በሥጋ አይነት ኑሮ እንኖር ነበር፣ ክርስቶስን ካወ ቅን በኋላ ግን፣ ከእንግዲህ ወዲህ በምንም በሥጋ አንኖርም።

ጆ.ስ.ት.፣ ገላትያ ፫፣፲፱–፳፡ ከገላትያ ፫፣፲፱–፳ ጋር አነጻፅሩ

የሙሴ የመጀመሪያው ቃል ኪዳን፣ ወይም የህግ፣ መካከለኛ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የአዲስ ኪዳን መካ ከለኛ ነው።

፲፱ እንግዲህ በዚህ በመጀመሪያው ቃል ኪዳን (በህግ) መካከለኛ እንዲሆን በመላእ ክት እጅ ለተሾመው ሙሴ በተሰጠው ህግ ውስጥ ተስፋው የተሰጠው ዘር እስኪመጣ ድረስ ህግ የተጨመረው በመተላለፍ ምክ ንያት ነበር።

፳ አሁን ይህ መካከለኛ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ አልነበረም፤ ነገር ግን አንድ የአ ዲስ ኪዳን መካከለኛ አለ፣ ለአብርሐም እና ለዘሩ ስለተሰጠው ቃል ኪዳን በሚመ ለከት በህግ ውስጥ እንደተጻፈው፣ ይህም ክርስቶስ ነው። አሁን ክርስቶስ የህይወት መካከለኛ ነው፤ ይህም እግዚአብሔር ለአ ብርሐም የገባው ቃል ኪዳን ነውና።

ጆ.ስ.ት.፣ ኤፌሶን ፬፣፳፯፤ ከኤፌሶን ፬፣፳፯ ጋር አነጻፅሩ

ከጽድቅ ያልሆነ ቁጣ ጎጥያት ነው።

፳፯ ትቆጣላችሁ፣ እና ኃጢአትንም አታደርጉምን? በቁጣችሁ ላይ ጸሀይ አት ጥለቅ፤

ጆ.ስ.ት.፣ ቁላስይስ ፪፣፳፯–፳፱፡ ከቁላስይስ ፪፣፳–፳፫ ጋር አነጻፅሩ

የሰዎች ትእዛዛት ራስን በመቆጣጠር አይነት ነገር ላይ ጥቅም ይኖረዋል፣ ግን እነርሱ እግዚአብሔርን አያክ ብሩም ወይም ሰውን አያድኑም።

፳፯ እነዚህ ሁሉ በመደረግ ሊጠፉ የተ ወሰኑት፣ አትያዝ፣ አትቅመስ፣ አትንካ ብለው ከሚያስተምሩት ሰዎች የመጡ ትምህርቶች እና ትእዛዛት የትኞቹ ናቸው?

፳፱ ይህ እንደ ምንም የእግዚአብሔር ክብር ሳይሆን፣ እንደ ገዛ ፈቃድህ በማም ለክና በትሕትና ሥጋንም በመጨቆን ሥጋ ያለ ልክ እንዳይጠግብ ለመከልከል ማድ ረግ፣ ጥበብ ያለው ይመስላል።

ጆ.ስ.ት.፣ ፮ ተሰሎንቄ ፬፣፲፫፡ ከ፮ ተሰሎንቄ ፬፣፲፫ ጋር አነጻፅሩ

ጌታ በሚመጣበት ጊዜ በህይወት የሚኖሩ ጻድቅ ሰዎች ከጻድቅ ሙታን የተለየ ምንም ልዩ እድል አይኖራቸ ውም።

፲፫ በጌታ ቃል የምንላችሁ ይህ ነውና፣

ሕያው ሆነው ጌታ እስኪመጣ ድረስ የሚ ቀሩት እነርሱም፣ ጌታ እስኪመጣ ድረስ የቀሩትን፣ ያንቀላፋቱን፣ አይቀድሙም።

ጆ.ስ.ት.፣ ፪ ተሰሎንቄ ፪፡፪–፫፣ ፯–፱። ከ፪ ተሰሎንቄ ፪፡፪–፱ ጋር አነጻፅሩ

ሰይጣን መውደቅን ወይም ክህደትን ጌታ ከመመለሱ በፊት ያመጣል።

፪ ይህን ከእኛ በመንፈስም ይሁን በቃል እስካልተቀበላችሁ ድረስ፣ የክርስቶስ ቀን ደርሶአል ብላችሁ ከአእምሮአችሁ ቶሎ እንዳትናወጡ፣ በደብዳቤዎችም እንዳ ትደነግጡም።

፫ ማንም በማናቸውም መንገድ አያስታ ችሁ፤ ክህደቱ አስቀድሞ ይመጣል፣ እና የዓመፅ ሰው እርሱም እንደ ጥፋት ልጅ ይገ ለጣልና።

፯ የዓመፅ ሚሥጥር አሁን ይሠራልና፣ አሁንም ይህን የሚሰራው እርሱ ነው፣ እና ከመንገድ የሚወገድበት እስከሚሟላ ጊዜ ድረስ እንዲሰራም ክርስቶስ ፈቅዶለታል።

፰ በዚያም ጊዜ ጌታ በአፉ መንፈስ የሚ ያጠፋው፣ በመመለሻው ብርሀን የሚሽረው ያ ዓመፀኛ ይገለጣል፤

፱ አዎን፣ ጌታ፣ እንዲሁም ኢየሱስ፣ በሰይጣን ሙሉ ሀይል፣ እና ምልክቶች፣ እናም በሀሰተኛ ድንቆችም አሠራር በኩል ክህደት እስከሚመጣ ድረስ መምጫው አይደርስም።

ጆ.ስ.ት.፣ ፮ ጢሞቴዎስ ፪፡፩። ከ፮ ጢሞቴዎስ ፪፡፩ ጋር አነጻፅሩ

ክርስቶስ አንድያ ልጅና መካከለኛ ነው።

፩ ሰዎች ሁሉ እንዲድኑና የእግዚአብ ሔር አንድያ ልጅ፣ እና በእግዚአብሔር እና በሰው መካከል አማላጅ እንዲሆን በተ መደበው፣ አንድ እግዚአብሔር በሆነው እና በሁሉም ሰዎች ላይ ሀይል በነበረው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የሆነውን እው ነቱን ወደ ማወቅ እንዲደርሱ የሚፈቅድ ማን ነው።

ጆ.ስ.ት.፣ ፮ ጢሞቴዎስ ፫፡፲፮–፲፯። ከ፮ ጢሞቴዎስ ፫፡፲፭–፲፯ ጋር አነጻፅሩ

ቤተክርቲያኗ የተመሰረተችው ኢየሱስ ስጋዊ ሆነ፣ ወንጌልን አስተማረ፣ እና ወደ አባቱ ተመለሰ በሚ ለው ዋና መሰረታዊ መርሆ ላይ ነው። በሚቀጥሉት ጥቅሶቶች ውስጥ ትኩረት በመስጠት የተቀየሩት ኢየ ሱስ ክርስቶስ "የእውነት አምድ እና ምድር" እንደሆነ አፅንኦት ለመስጠት ነው።

፲፭ ብዘገይ ግን፣ በእግዚአብሔር ማደ ሪያ ቤት፣ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክር ስቲያን፣ መኖር እንዴት እንደሚገባ ታውቅ ዘንድ እጽፍልሃለሁ።

፲፮ የእውነት ዓምድና መሠረት፣ (እግ ዚአብሔርንም የመምሰል ምሥጢር ያለ ጥርጥር ታላቅ ነው፣) እግዚአብሔር በሥጋ የተገለጠበት፥ በመንፈስ የጸደቀበት፥ ለመ ላእክት የታየበት፥ በአሕዛብ የተሰበከበት፥ በዓለም የታመነበት፥ በክብር ያረገበት ነው።

ጆ.ስ.ት.፣ ፮ ጢሞቴዎስ ፮፡፲፭–፲፮። ከ፮ ጢሞቴዎስ ፮፡፲፭–፲፮ ጋር አነጻፅሩ

የዘለአለማዊ ህይወት (የወንጌል) ብርሀን በውስጣቸው የሚኖርላቸው ኢየሱስን ማየት ይችላሉ።

፲፭ ያንም በራሱ ጊዜ፣ ብፁዕና ብቻውን የሆነ ገዥ የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ ያሳያል፣ ለእርሱ ክብርና የዘላለም ኃይል ይሁን።

፲፮ እርሱን አንድ ሰው እንኳ አላየ ውም፣ ሊያይም አይቻለውም፣ ማንም ሊቀርበውም አይችልም፣ እርሱም ብቻ የዘለአለማዊ ህይወት ብርሃንና ተስፋ በው ስጡ ይኖራል።

ጆ.ስ.ት.፣ ዕብራውያን ፩፡፲–፲፣ ፲፪–፲፫። ከዕብራውያን ፩፡፲–፲፣ ፲፪–፲፫ ጋር አነጻፅሩ

መላእክት አገልጋይ መንፈሶች ናቸው።

፲ ደግሞም በኵርን ወደ ዓለም ሲያገባ፣ የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉም አገልግ ሎቱን እንደ እሳት ነበልባል ለሚያደርገው ለእርሱ ይስገዱ ይላል።

፲ ስለ መላእክትም፣ መላእክቱ አገል ጋይ መናፍስት ናቸው አለ።

ጆ.ስ.ት.፣ ዕብራውያን ፩፡፣ ፲።

ከዕብራውያን ፩፡፣ ፲ ጋር አነጻፅሩ

ልባቸውን የሚያደነድኑ አይድኑም፤ ንስሀ የሚገቡ ወደ ጌታ እረፍት ይገባሉ።

፲ የእግዚአብሔር ሥራዎች ዓለም ከተፈ ጠረ ጀምሮ ምንም እንኳ የተዘጋጀ (ወይም የተፈጸመ) ቢሆን፤ ልቦቻቸውን ካጠ ጠሩ ወደ ዕረፍቴ አይገቡም ብዬ በቁጣዬ ማልሁ፤ ደግሞም ልቦቻቸውን ካላጠጠሩ ወደ እረፍቴ ይገባሉ ብዬ ማልሁ እንዳለ፣ እኛስ ያመንን ወደ ዕረፍቱ እንገባለን።

ጆ.ስ.ት.፣ ዕብራውያን ፮፡፣ ፩–፲፡

ከዕብራውያን ፮፡፣ ፩–፲ ጋር አነጻፅሩ

የክርስቶስ ትምህርት መሰረታዊ መርሆች ወደ ፍጹም ነት ይመራሉ።

፩ ስለዚህ የክርስቶስ መሰረታዊ መርሆ ችን ሳንተው ወደ ፍጻሜ እንሂድ፤ ከሞተ ሥራ ንስሐ፣ እና በእግዚአብሔር እምነት መሠረትን ደግመን አንመሥርት።

፪ ንስሐና በእግዚአብሔር እምነት፥ ስለ ጥምቀቶችና እጆችንም ስለ መጫን ስለ ሙታንም ትንሣኤ ስለ ዘላለም ፍርድም ትምህርትም።

፫ እግዚአብሔርም ቢፈቅድ ወደ ፍጻሜም እንሄዳለን።

፬ አንድ ጊዜ ብርሃን የበራላቸውን ሰማ ያዊውንም ስጦታ የቀመሱትን ከመንፈስ ቅዱስም ተካፋዮች ሆነው የነበሩትን፣

፭ መልካሙንም የእግዚአብሔርን ቃልና ሊመጣ ያለውን የዓለም ኃይል የቀመሱትን፣

፮ በኋላም የካዱትን በንስሐ እንደገና እንዲታደሱም የማይቻል አድርጓል፤ ለራ ሳቸው የእግዚአብሔርን ልጅ ይሰቅሉታል፣ እናም ያዋርዱትማልና።

፯ ብዙ ጊዜ በእርስዋ ላይ የሚወርደውን ዝናብ የምትጠጣ መሬት፥ ለሚያርሱአትም ደግሞ ለሚኖሩባትም የምትጠቅምን አት ክልት የምታበቅል፥ ከእግዚአብሔር በረከ ትን ታገኛለችና፣ በእሳትም የምትጸዳበት ቀን ይመጣል።

፰ እሾህና ኵርንችትን ግን ብታወጣ፥ የተጣለች ናት ለመረገምም ትቀርባለች፤ ስለዚህ መልካም ፍሬ የማያመጡ፣ ወደ እሳት ይጣላሉ፤ መጨረሻቸውም መቃ ጠል ነው።

፱ ስለ እናንተ ግን፥ ወዳጆች ሆይ፥ ምንም እንኳ እንዲሁ ብንናገር፥ አብልጦ የሚሻለውና ለመዳን የሚሆነው እንዲሆን ላችሁ ተረድተናል።

፲ ስለዚህ እግዚአብሔር፥ ቅዱሳንን ስላ ገለገላችሁ እስከ አሁንም ስለምታገለግሉአ ቸው፥ ያደረጋችሁትን ሥራ ለስሙም ያሳ ያችሁትን ፍቅር ይረሳ ዘንድ ዓመፀኛ አይ ደለምና።

ጆ.ስ.ት.፣ ዕብራውያን ፯፡፣ ፲፡

ከዕብራውያን ፯፡፣ ፲ ጋር አነጻፅሩ

መልከ ጼዴቅ በእግዚአብሔር ልጅ ስርዓት ቅዱሱ ካህን ነበር። ይህን ክህነት የሚቀበሉ ጉሉ እንደ እግዚ አብሔር ልጅ ለመሆን ይችላሉ።

፲ ይህ የመልከ ጼዴቅ አባትና እናት የት ውልድም ቍጥር እንደሌለው፣ ለዘመኑም ጥንት ለህይወቱም ፍጻሜ እንደሌለውም፣ እንደ እግዚአብሔር ልጅ ስርዓት ወደካህ ንነት ተሾመ። እና ወደ ክህነት የተሾሙት ሁሉ በእግዚአብሔር ልጅ ተመስለው ለዘ ላለም ካህን ሆነው ይኖራሉ።

ጆ.ስ.ት.፣ ዕብራውያን ፯፡፣ ፲፱–፳፩። ከዕብራውያን ፯፡፣ ፲፱–፳፩ ጋር አነጻፅሩ

ህግ “ለሚሻል ኪዳን ዋስ” ለሆነው ለኢየሱስ ህዝብን አዘጋጀ።

፲፱ ሕጉ ያለ መሀላ ይፈጸማል እናም ምንም ፍጹም አላደረገምና፣ ግን ወደ እግ ዚአብሔርም የምንቀርብበት የሚሻል ተስፋ ገብቶአል።

፳ ይህ ሊቀ ካህን ያለ መሐላ እንደማ ይሆን፤ በዚህም ኢየሱስ ለሚሻል ኪዳን ዋስ ሆኖአል።

፳፩ (እርሱ ግን፣ ጌታ፣ አንተ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ካህን ነህ ብሎ ማለ አይጸጸትም ብሎ በተናገረለት ከመሐላ ጋር ካህን ሆኖአልና ያለ መሐላ ካህን እንዳልሆነ መጠን፤)

ጆ.ስ.ት.፣ ዕብራውያን ፯፡፳፩–፳፭። ከዕብራውያን ፯፡፳፩–፳፭ ጋር አነጻፅሩ

ክርስቶስ ለኃጢያቶቻችን እራሱን ኃጢያት እንደሌለው መስዋዕት አቀረበ።

፳፩ ቅዱስና ያለ ተንኮል ነውርም የሌለ በት ከኃጢአተኞችም የተለየ ከሰማያትም ገዝ የሆነ፣ እንደዚህ ያለ ሊቀ ካህን እንድ ንሆን ይገባልና፤

፳፪ እርሱም አስቀድሞ ለራሳቸው ኃጢ አት በኋላም ስለ ሕዝቡ ኃጢአት ዕለት ዕለት መሥዋዕትን እንደሚያቀርቡት እን ደነዚያ ሊቀ ካህናት አይደለም፤ ከህዝቦች ኀጥያቶች በስተቀር፣ ለራሱ ኃጢያቶች መስዋዕት ማቅረብ የለበትም፣ ምንም ኀጥ ያት አያውቅምና። ራሱንም ባቀረበ ጊዜ ይህን አንድ ጊዜ ፈጽሞ አድርጎአልና።

ጆ.ስ.ት.፣ ዕብራውያን ፲፪፡፩። ከዕብራውያን ፲፪፡፩ ጋር አነጻፅሩ

እምነት ተስፋ የተደረገባቸውን ነገሮችን ማረጋገጫ ነው።

፩ እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያረጋግጥ፣ የማናየውንም ነገር የሚያ ስረዳ ነው።

ጆ.ስ.ት.፣ ዕብራውያን ፲፪፡፴፭። ከዕብራውያን ፲፪፡፴፭ ጋር አነጻፅሩ

ለክርስቶስ የሚሰቃዩ ታማኞች የመጀመሪያውን ትን ሳኤ ያገኛሉ።

፴፭ ሴቶች ሙታናቸውን በትንሣኤ ተቀ በሉ፤ ሌሎችም መዳንን ሳይቀበሉ የሚበ ልጠውን የመጀመሪያ ትንሣኤ እንዲያገኙ እስከ ሞት ድረስ ተደበደቡ፤

ጆ.ስ.ት.፣ ያዕቆብ ፩፡፪። ከያዕቆብ ፩፡፪ ጋር አነጻፅሩ

ፈተናዎች ሳይሆን ስቃዮች ለመቀደስ ይረዱናል።

፪ ወንድሞቼ ሆይ፣ ብዙ ስቃዮች ሲደር ስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቍጠሩት፤

ጆ.ስ.ት.፣ ያዕቆብ ፪፡፩። ከያዕቆብ ፪፡፩ ጋር አነጻፅሩ

አባላት አንድን ሰው ከሌላ በላይ ከፍ አድርገው አይ መልከቱ።

፩ ወንድሞቼ ሆይ፥ ለሰው ፊት እያደ ላችሁ፣ በክብር ጌታ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት ሊኖራችሁ አትችሉም።

ጆ.ስ.ት.፣ ያዕቆብ ፪፡፲፬–፳፪። ከያዕቆብ ፪፡፲፬–፳፪ ጋር አነጻፅሩ

እምነት ያለስራ የሞተ ነው እናም አያድንም።

፲፬ ወንድሞቼ ሆይ፥ እምነት አለኝ የሚል፥ ሥራ ግን የሌለው ሰው ቢኖር ይህ ምን ይጠቅመዋል? እምነቱስ ሊያድነው ይችላልን?

፲፭ አዎን፣ አንድ ሰው፣ እምነት ያለ ሥራ እንዳለኝ አሳይሀለሁ ይል ይሆናል፣ ግን እኔም እምነትህን ያለስራዎችህ አሳ የኝ፣ እና እምነቴን በሥራዎቼ አሳይሃለሁ እላለሁ።

፲፮ ወንድም ወይም እኅት ራቁታቸውን ቢሆኑ የዕለት ምግብንም ቢያጡ፥ ከእናንተ አንዱም፣ በደኅና ሂዱ፣ እሳት ሙቁ፥ ጥገ ቡም ቢላቸው፤ ለሰውነት ግን የሚያስፈል ጉትን ባይሰጣቸው፤ ለዚህ አይነት እምነ ትህ ምን ይጠቅማል?

፲፯ እንደዚሁም ሥራ የሌለው እምነት ቢኖር በራሱ የሞተ ነው።

፲፰ ስለዚህ፣ አንተ ከንቱ ሰው፥ እምነት ከሥራ ተለይቶ የሞተ መሆኑን እና ሊያድ ንህ እንደማይችል ልታውቅ ትወዳለህን?

፲፱ እግዚአብሔር አንድ እንደ ሆነ አንተ ታምናለህ፤ መልካም ታደርጋለህ፤ አጋ ንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል፤ ራስህን እንደነርሱ አድርገሀል፣ ጻድቅ ባለ መሆን።

፳ አባታችን አብርሃም ልጁን ይስሐ ቅን በመሠዊያው ባቀረበ ጊዜ በሥራ የጸ ደቀ አልነበረምን?

፳፩ እምነት ከሥራው ጋር አብሮ ያደ ርግ እንደ ነበረ፣ በሥራም እምነት ፍጹም እንደሆነ ትመለከታለህን?

ጆ.ስ.ት.፣ ፮ ጴጥሮስ ፫፡፳፡፡
ከ፮ ጴጥሮስ ፫፡፳ ጋር አነጻፅሩ

በወህኒ ቤት ውስጥ ያሉት አንዳንድ መንፈሶች በኖኅ ቀናት ውስጥ ጻድቃን አልነበሩም።

፳ ጥቂቶች ማለት ስምንት ነፍስ በውኃ የዳኑበት መርከብ ሲዘጋጅ፣ የእግዚአብሔር ትዕግሥት በኖኅ ዘመን በቆየ ጊዜ፣ አንዳን ዶች በኖኅ ቀናት ታዛዥ አለነበሩም።

ጆ.ስ.ት.፣ ፮ ጴጥሮስ ፬፡፮፡፡
ከ፮ ጴጥሮስ ፬፡፮ ጋር አነጻፅሩ

ወንጌሉ ለሙታን ተሰብኳል።

፮ እንደሰዎች በሥጋ እንዲፈረድባቸው በመንፈስ ግን በእግዚአብሔር ፈቃድ እን ዲኖሩ፣ ስለዚህ ምክንያት ወንጌል ለሙ ታን ደግሞ ተሰብኮላቸው ነበርና።

ጆ.ስ.ት.፣ ፮ ጴጥሮስ ፬፡፳፡፡
ከ፮ ጴጥሮስ ፬፡፳ ጋር አነጻፅሩ

ልግስና ኃጢያትን ከመስራት ያግደናል።

፳ እና ከሁሉም ነገሮች በላይ እርስ በራ ሳችሁ መካከል ልባዊ ልግስና ይኑራችሁ፤ ልግስና የተባዙ ኀጥያቶችን ያስወግዳልና።

ጆ.ስ.ት.፣ ፪ ጴጥሮስ ፫፡፫–፲፫፡፡
ከ፪ ጴጥሮስ ፫፡፫–፲፫ ጋር አነጻፅሩ

በመጨረሻው ቀናት፣ ብዙ ሰዎች ጌታ ኢየሱስ ክርስ ቶስን ይክዳሉ። ሲመጣም፣ ብዙ የፍጥር መዓቶች ይደ ርሳሉ። በጻድቅነት ከጸናን፣ አዲስ ምድር እንቀበላለን።

፫ በመጨረሻው ዘመን እንደ ራሳቸው ምኞት የሚመላለሱ ዘባቾች በመዘበት እን ዲመጡ ይህን በፊት እወቁ።

፬ እነርሱም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በመካድ፣ እና የመምጣቱ የተስፋ ቃል ወዴት ነው? አባቶች ከሞቱባት ጊዜ፥ ሁሉም ነገሮች እንዳሉ መቀጠል አለባ ቸው፣ እናም ከፍጥረት መጀመሪያ ይዞ ሁሉ እንዳለ ይኖራልና ይላሉ።

፭ ሰማያት ከጥንት ጀምረው ምድርም በእግዚአብሔር ቃል ከውኃ ተጋጥማ በውኃ መካከል ወጥታ እንደ ነበሩ ወደው አያስተውሉምና፤

፮ እናም በእግዚአብሔር ቃል፣ በዚ ህም ምክንያት ያን ጊዜ የነበረ ዓለም በውኃ ሰጥሞ ጠፋ፤

፯ አሁን ያሉ ሰማያትና ምድር ግን እግ ዚአብሔርን የማያመልኩት ሰዎች እስከሚ ጠፉበት እስከ ፍርድ ቀን ድረስ ተጠብቀው በዚያ ቃል ለእሳት ቀርተዋል።

፰ የጌታ መምጣትን በሚመለከት ግን፣ እናንተ ወዳጆች ሆይ፥ በጌታ ዘንድ አንድ ቀን እንደ ሺህ ዓመት፥ ሺህ ዓመትም እንደ አንድ ቀን እንደ ሆነ ይህን አንድ ነገር አት ርሱ።

፱ ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስ ላቸው ጌታ ስለ ተስፋ እና መምጣት ቃሉ አይዘገይም፥ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እን ዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እኛ ይታገሣል።

፲ የጌታው ቀን ግን እንደ ሌባ ሆኖ ይመ ጣል፤ በዚያም ቀን ሰማያት ይንቀጠቀ ጣሉ፣ እናም ምድር ደግሞም ትንቀጠቀ ጣለች ተራራዎችም ይቀልጣሉ፣ በታላቅ ድምጽም ያልፋሉ፣ ፍጥረት በትልቅ ትኵ ሳት ይሞላል፣ ምድርም ትሞላለች፣ በእ ርስዋም ላይ የተደረገው እርኩስ ስራ ሁሉ ይቃጠላል።

፲፩ እነዚህ ሁሉ የሚደመሰሱ ከሆኑ፣ በቅዱስ ኑሮ እግዚአብሔርንም በመምሰል እንደ ምን ልትሆኑ ይገባችኋል፣

፲፪ የሰማያት የተረከሱት ነገሮች ተቃጥ ለው፣ በሚቀልጡበት፣ ተራራዎች በትልቅ ትኵሳት በሚቀልጡበት፣ የጌታ መምጣት ቀን ስትጠብቁና ስትዘጋጁም?

፲፫ ነገር ግን፣ ከጸናን፣ እንደ ተስፋ ቃሉ እንጠብቃለን። ጽድቅ የሚኖርባትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንጠብቃለን።

ጆ.ስ.ት.፣ ፮ ዮሐንስ ፪፡፮።
ከ፮ ዮሐንስ ፪፡፮ ጋር አነጻፅሩ

ንስሀ ከገባን ክርስቶስ ከአብ ጋር አማላጃችን ነው።

፮ ልጆቼ ሆይ፣ ኃጢአትን እንዳታደ ርጉ ይህን እጽፍላችኋለሁ። ማንም ኃጢ አትን ቢያደርግ እና *ንስሀ ቢገባ* ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

ጆ.ስ.ት.፣ ፮ ዮሐንስ ፫፡፱።
ከ፮ ዮሐንስ ፫፡፱ ጋር አነጻፅሩ

ከእግዚአብሔር የተወለደ በኀጥያት አይቀጥልም።

፱ ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ በኃጢ አት አይቀጥልም፣ *የእግዚአብሔር መን ፈስ* በእርሱ ይኖራልና፤ እና በኀጥያት መቀ ጠል አይችልም፣ ምክንያቱም *ቅዱስ የተ ሰፋ መንፈስን በመቀበሉ* ከእግዚአብሔ ርም ተወልዶአልና።

ጆ.ስ.ት.፣ ፮ ዮሐንስ ፤፡፲፪።
ከ፮ ዮሐንስ ፤፡፲፪ ጋር አነጻፅሩ

በእግዚአብሔር የሚያምኑ ሰዎች ብቻ ናቸው ሊያዩት የሚችሉት።

፲፪ *ከሚያምኑት በስተቀር*፣ እግዚአብ ሔርን ማንም ሰው ከቶ አላየውም። እርስ በርሳችን ብንዋደድ፣ እግዚአብሔር በእኛ ይኖራል ፍቅሩም በእኛ ፍጹም ሆኖአል።

ጆ.ስ.ት.፣ *ራዕይ* ፮፡፮–፱። ከራዕይ ፮፡፮–፰ ጋር አነጻፅሩ

ሐዋርያው ዮሐንስ በዮሐንስ ራዕይ ውስጥ ትንቢቶች ተቀበለ። በኢየሱስ ክርስቶስ እና በመልአክ ተጎበኘ።

፮ ቶሎ ይሆን ዘንድ የሚገባውን ነገር ለባ ሪያዎቹ ያሳይ ዘንድ፣ በመልአኩ ልኮ ለባ ሪያው ለዮሐንስ ያመለከተው፣ *ከኢየሱስ ክርስቶስ* የተሰጠው *የእግዚአብሔር አገ ልጋይ የዮሐንስ ራዕይ*፣

፪ እርሱም ለእግዚአብሔር ቃልና ለኢ የሱስ ክርስቶስ ምስክር ላየውም ሁሉ *የመ ሰከረው*።

፫ *የጌታ መምጫ ዘመኑ ቀርቦአልና* የሚ ያነቡት የትንቢቱን ቃል የሚሰሙትና *የሚ ረዳቸው*፣ በውስጡ የተጻፈውን የሚጠብ ቁት ብፁዓን ናቸው።

፬ *አሁን ይህ ዮሐንስ* በእስያ ላሉት ለሰ ባቱ ቤተክርስቲያናት *አገልጋዮች የሰጠው ምስክር ነው*። *ካለውና ከነበረው ከሚመ ጣውም*፣ *የሰባት ቤተክርስቲያናት ሰባት አገልጋሎች ለሆኑት እንደመሰክሩ* በዙፋ ኑም ፊት *መላእክቱን ከላከው*፣ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።

፭ *ስለዚህ*፣ *እኔ*፣ *ዮሐንስ*፣ *ታማኝ ምስ ክር*፣ ከመላእክ እና ከሙታንም በኵር እና *የምድርም ነገሥታት ገዥ ከሆነ* ከኢየሱስ ክርስቶስ *ለእኔ ስለተሰጡኝ ነገሮች እመ ሰክራለሁ*።

፮ ለወደደን፣ ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን፣ ለእግዚአብሔር ለአባቱም ካህናት እንድንሆን ላደረገ፣ *ክብር ይሁን*። ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ክብርና ኃይል ይሁን፤ አሜን።

፯ *እነሆ*፣ በደመና *በመንግስት ውስጥ ካሉት አስር ሺህ ቅዱሳን ጋር*፣ *በአባቱ ክብር ተለብሶ ይመጣል*፤ ዓይንም ሁሉ ያዩታል፤ እና የወጉትም፣ የምድርም ወገ ኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ። እን ዲሁም ይሁን፣ አሜን።

፰ *እንዲህም ብሏልና*፣ *ያለውና የነበ ረው የሚመጣውም* ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ፣ አልፋና *ዖሜጋ* እኔ ነኝ።

ጆ.ስ.ት.፣ *ራዕይ* ፪፡፳፪። ከራዕይ ፪፡፳፪ ጋር አነጻፅሩ

ክፉዎች ወደገሀነም ይጣላሉ።

፳፪ እነሆ፣ *በገሀነም* ላይ እጥላታለሁ፣ ከእርስዋም ጋር የሚያመነዝሩትን ከ*ሥራዋ* ንስሐ ባይገቡ በታላቅ መከራ እጥላቸዋለሁ፤

ጆ.ስ.ት.፣ *ራዕይ* ፪፡፳፯–፳፱። ከራዕይ ፪፡፳፯–፳፱ ጋር አነጻፅሩ

የክርስቶስ ትእዛዛትን በማክበር አለምን የሚያሸንፉ በሚመጣው አለም መንግስቶችን በእምነት፣ በእኩል ነት፣ በፍትህ ይገዛሉ።

፳፯ ድል ለነሣውና እስከ መጨረሻም

ትእዛዛቴን ለጠበቀው፣ በብዙ መንግስት ቶች ሥልጣንን እሰጠዋለሁ፥

፳፯ እርሱም በእግዚአብሔር ቃል ይገ ዛቸዋል፤ እናም እነርሱም በእጁ ውስጥ ጭቃወ እቃ በሸክላ ሠሪ እጅ እንዳለ ይሆ ናሉ፤ እናም በእምነት፣ በእኩልነት፣ እና በፍትህ፣ እንዲሁም እኔ ደግሞ ከአባቴ እንደ ተቀበልሁ ይገዛቸዋል።

ጆ.ስ.ት.፣ ራዕይ ፭፥፮። ከራዕይ ፭፥፮ ጋር አነጻፅሩ

አስራ ሁለት የእግዚአብሔር አገልጋዮች በምድር ሁሉ ተልከዋል።

፮ በዙፋኑና በአራቱ እንስሶች መካከልም በሽማግሌዎችም መካከል እንደ ታረደ በግ ቆሞ አየሁ፣ አስራ ሁለት ቀንዶችና አስራ ሩለት ዓይኖች ነበሩት እነርሱም ወደ ምድር ሁሉ የተላኩ አስራ ሁለት የእግዚ አብሔር አገልጋዮች ናቸው።

ጆ.ስ.ት.፣ ራዕይ ፲፪፥፩–፲፯። ከራዕይ ፲፪፥፩–፲፯ ጋር አነጻፅሩ

ዮሐንስ የሴቷን፣ የልጅ፣ የብረት በትርን፣ የዘንዶ ውን፣ እና የሚካኤልን ምሳሌዎች ገለጻቸው። በሰማይ የተጀመረው ጦርነት በምድር ቀጥሏል። በጆ.ስ.ት. ውስጥ የአንቀጾች ተከታታይነት እንዴት እንደተቀ የረ ተመልከቱ።

፩ በምድር ላይ ነገሮች እንዳሉት የሚ መሳሰል ታላቅ ምልክትም በሰማይ ታየ፤ ፀሐይን ተጐናጽፋ ጨረቃ ከእግሮችዋ በታች ያላት በራስዋም ላይ የአሥራ ሁለት ከዋክብት አክሊል የሆነላት አንዲት ሴት ነበረች።

፪ እርስዋም ፀንሳ ነበር ምጥም ተይዛ ልትወልድ ተጭንቃ ጮኸች።

፫ በብረት በትር ሁሉንም ህዝቦች የሚ ገዛ ወንድ ልጅንም ወለደች፤ ልጁ ም ወደ እግዚአብሔር እና ወደ ዙፋኑ ተወሰደ።

፬ ሌላም ምልክት በሰማይ ታየ፤ እነሆም ታላቅ ቀይ ዘንዶ፤ ሰባት ራሶችና አሥር ቀን ዶችም ነበሩት በራሶቹም ላይ ሰባት ዘው ዶች ነበሩ። ጅራቱም የሰማይን ከዋክብት ሲሶ እየሳበ ወደ ምድር ጣላቸው። ዘንዶ ውም ሴቲቱ በወለደች ጊዜ ሕፃንዋን እን ዲበላ ዘንድ በፊቷ ቆመ።

፭ ሴቲቱም ሺህ ከሁለት መቶ ስድሳ አመታት በዚያ እንዲመገቡአት በእግዚ አብሔር ተዘጋጅቶላት ወደ ነበረው ስፍራ ወደ በረሀ ሸሸች።

፮ በሰማይም ሰልፍ ሆነ፤ ሚካኤልና መላ እክቱ ዘንዶውን ተዋጉ፤ ዘንዶውና መላእ ክቱም ከሚካኤል ጋር ተዋጋ፤

፯ ዘንዶውም ሚካኤልን፣ ወይም ሕጻ ኑን፣ ወይም የእግዚአብሔር ቤተክርስቲ ያን የሆነችውን፣ ከስቃዮዋ የዳነችውን፣ እና የእኛ እግዚአብሔርንና የክርስቶስን መንግስት ያመጣችውን ሴት አላሸነፈም።

፰ ከዚያም ወዲያ ለተጣለው፣ ዲያ ብሎስ እና ደግሞም ሰይጣን ለሚባለው የድሮው እባብ፣ አለምን ሁሉ ላታለለው ለታላቁ ዘንዶ በሰማይ ስፍራ አልተገኘለ ትም፤ ወደምድርም ተጣለ፤ መላእክቶቹም ከእርሱ ጋር ተጣሉ።

፱ ታላቅም ድምፅ በሰማይ ሰማሁ እን ዲህ ሲል ሰማሁ፣ አሁን የአምላካችን ማዳ ንና ኃይል መንግሥትም የክርስቶስም ሥል ጣን መጣ።

፲ ቀንና ሌሊትም በአምላካችን ፊት የሚከሳቸው የወንድሞቻችን ከሳሽ ተጥ ሎአልና።

፲፩ እነርሱም ከበጉ ደም የተነሣ ከምስ ክራቸውም ቃል የተነሣ ድል ነሡት፤ ነፍ ሳቸውንም አልወደዱምና፣ ምስክራቸውን ግን እስከ ሞት ድረስ ጠበቁ። ስለዚህ፣ ሰማ ያትና በውስጡ የምታድሩ ሆይ፣ ደስ ይበ ላችሁ።

፲፪ ከእነዚህ ነገሮች በኋላ ሌላ ድምፅ እንዲህ ሲል ሰማሁ፣ ለምድር ለሚኖ ሩትና፣ አዎን፣ እናም በባሕር ደሴቶች ለሚያድሩት ወዮላቸው! ዲያብሎስ ጥቂት ዘመን እንዳለው አውቆ በታላቅ ቍጣ ወደ እናንተ ወርዶአልና።

፲፫ ዘንዶውም ወደ ምድር እንደ ተጣለ በማየቱ ምክንያት፣ ወንድ ልጅ የወለደች ውን ሴት አሳደዳትና።

፲፬ ስለዚህ፣ ከእባቡም ፊት ተሰድዳ አንድ ዘመን፣ ዘመናትም፣ የዘመንም እኵሌታ ወደ ምትመገብበት ወደ ስፍራዋ ወደ በረሀ እንድትበር ለሴቲቱ ሁለት የታላቁ ንሥር ክንፎች ተሰጣት።

፲፭ እባቡም ሴቲቱ በወንዝ እንድትወሰድ ሊያደርግ ወንዝ የሚያህልን ውኃ ከአፉ በስ ተጓላዋ አፈሰሰ።

፲፮ ምድሪቱም ሴቲቱን ረዳቻት፣ ምድሪቱም አፍዋን ከፍታ ዘንዶው ከአፉ ያፈሰሰውን ወንዝ ዋጠችው።

፲፯ ስለዚህ፣ ዘንዶውም በሴቲቱ ላይ ተቈጥቶ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁትን የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር ያላቸውን ከዘርዋ የቀሩትን ሊዋጋ ሄደ።

ጆ.ስ.ት.፣ ራዕይ ፲፪፡፲፭፣ ፳፩።

ከራዕይ፲፪፡፲፭፣ ፳፩ ጋር አነጻፅሩ

እግዚአብሔር የክርስቶስን ቃል በመጠቀም ህዝቦችን ይመታል።

፲፭ ከአፉም የእግዚአብሔር ቃል ይወጣል፣ በዚህም አሕዛብንም ይመታበታል፤ በአፉ ቃልም ይገዛቸዋል፤ እርሱም ሁሉን በሚገዛ እግዚአብሔር የብርቱ ቁጣ ወይን መጭመቂያን ይረግጣል።

፳፩ የቀሩትም በፈረስ ላይ ከተቀመጠው ቃል ተገደሉ፣ ቃልም ከአፉ የሚወጣው ነበር፤ ወፎችም ሁሉ ከሥጋቸው ጠገቡ።

የመፅሐፍ ቅዱስ ካርታዎች

የሚቀጥሉት ካርታዎች ቁድሳት መጻህፍትን ለመርዳት ይረዷችኋል። በቅዱሳት መጻህፍት ውስጥ የሚወያዩትን የምድር ጂኦግራፊ በማወቅ፣ የቅዱሳት መጻህፍት ድርጊቶችን ለመረዳት ትችላላችሁ።

ማጠቃለያና ቁልፎች

ከእዚህ በታች ያሉት ካርታዎች ዋና ሀሳቦች የሚቀጥሉት ቁጥር የተሰጣቸውን ካርታዎች ላይ የሚያተኩሩ ናቸው። እነ ዚህ ካርታዎች ታላቅ ክፍለ አገሮችን እና በመልክአ ምድራዊ አካባቢዎች ላይ የሚያተኩሩ ናቸው።

1. የቅዱስ ምድር የተፈጥሮአዊ ነገሮች ካርታ
2. የእስራኤል ከግብፅ መሰደድ እና ወደ ከነዓን መግባት
3. የ፲፪ ጎሳዎች መከፋፈል
4. የዳዊት እና የሰለሞን ግዛት
5. የአሶር ግዛት
6. አዲሱ የባቢሎን ግዛት (ናቡከደነፆር) እና የግብፅ ግዛት
7. የፋርሳዊ ግዛት
8. የሮሜ ግዛት
9. የብሉይ ኪዳን አለም
10. ከነዓን በብሉይ ኪዳን ዘመናት
11. ቅዱስ ምድር በአዲስ ኪዳን ዘመናት
12. ኢየሩሳሌም በኢየሱስ ጊዜ
13. የሐዋርያው ጳውሎስ የሚስዮን ጉዞ
14. የቅዱስ ምድር ከፍታ



የሚቀጥለው በካርታዎች ላይ የሚጠቀሙባቸውን የተለያዩ ምልክቶች እና ልዩ የፊደል አጣጣሎች ልትረዱበት የምትች ሉበት ቁልፍ ነው። በተጨማሪም፣ እያንዳንዱ ካርታዎች ስለአንዱ ካርታ ተጨማሪ ምልክቶች መግለጫ ይኖራቸዋል።

●	ቀይ ነጥብ ከተማን ያመለክታል።
▲	ትንሹ ጥቁር ሶስት ማዕዘን ተራራን ያመልክታል።
የሙት ባህር	ይህ ልዩ የፊደል አጣጣል አብዛኛውን ጊዜ የስነ መልክአ ምድር ቦታን፣ ለምሳሌ ባህሮችን፣ ወንዞችን፣ ተራራዎችን፣ በረሀዎችን፣ እና ደሴቶችን፣ ለማመልከት ይጠቀሙበታል።
ኢየሩሳሌም	ይህ ልዩ የፊደል አጣጣል ከተማዎችን ለመጠቆም ይጠቀሙበታል (እናም በኢየሩሳሌም ከተማ ካርታ ላይ ልዩ ቦታን ይጠቁማል)።
ሞአብ	ይህ ልዩ የፊደል አጣጣል እንደ ክልሎች፣ ህዝቦች፣ እና ጎሳዎች አይነት ትንሽ የፖለቲካ ክፍሎችን ለመጠቆም ይጠቀሙበታል።
ይሁዳ	ይህ ልዩ የፊደል አጣጣል እንደ ግዛት እና ህዝቦች አይነት ትልቅ የፖለቲካ ክፍሎችን ለመጠቆም ይጠቀሙበታል።

1. የቅዱስ ምድር የተፈጥሮአዊ ነገሮች ካርታ

2. የእስራኤል ከግብፅ መሰደድ እና ወደ ከነዓን መግባት



1. ራምሴ እስራኤል ከግብፅ ተጥላ ነበር (ዘፀአ. ፲፪፤ ዘኁል. ፴፫፡፭)።
2. ሱኮት ዕብራውያን የመጀመሪያውን የሰፈሩበትን ቦታ ለቅቀው ሲሄዱ፣ ጌታ በቀን በዳመና እናም በሌሊት በእሳት ዓምድ ረዳቸው (ዘፀአ. ፲፫፡፳–፳፪)።
3. በፊሀሒሮት እስራኤል በቀይ ባህር በኩል አለፉ (ዘፀአ. ፲፬፤ ዘኁል. ፴፫፡፯)።
4. ማራ ጌታ የማራን ውሀዎች ፈወሰ (ዘፀአ. ፲፭፡፳፫–፳፭)።
5. ኤሊም እስራኤል በ፲፪ ምንጮች አጠገብ ሰፈሩ (ዘፀአ. ፲፭፡፳፯)።
6. የሲን ምድረበዳ ጌታ እስራኤልን ለመመገብ መና እና ኩዌል ላከ(ዘፀአ. ፲፮)።
7. ራፊዲም እስራኤል ከአማሌቅ ጋር ተዋጉ (ዘፀአ. ፲፯፡፰–፲፮)።
8. የሲና ተራራ (የኮሬብ ተራራ ወይም ጀቤል ሙሳ) ጌታ አስር ቃላትን ገለጸ (ዘፀአ. ፲፱–፳)።
9. የሲና ምድረበዳ እስራኤል ታቦት ሰራች (ዘፀአ. ፳፭–፴)።
10. የምድረበዳ መስፈሪያ ቦታ ሰባ ሽማግሌዎች ሙሴን ህዝቡን በመግዛት እንዲረዱት ተጠሩ (ዘኁል. ፲፩፡፲፮–፲፯)።
11. ዔጽዮንጋብር እስራኤል በኤሳው እና በአሞን ህዝቦች ምድር ውስጥ አለፉ (ዘዳግ. ፪)።
12. ቃዴስ በርኔ ሙሴ ሰላዮች ወደ ቃል ኪዳን ምድር ላከ፤ እስራኤል አመጸች እና ወደ ምድሯ አልገባችም፤ ቃዴስ እንደ እስራኤል ዋና መስፈሪያ ቦታ አገለገለ (ዘኁል. ፲፫፡፩–፫፣ ፲፯–፴፫፣ ፲፱፡፴፣ ፴፫፡፴፣ ፴፮፡፲ ዘዳግ. ፪፡፲፬)።
13. የምስራቅ ምድረበዳ እስራኤል ከኤዶም እና ከሞአብ ጋር መዋጋትን አስወገዱ (ዘኁል. ፳፡፲፱–፳፩፣ ፳፪–፳፭)።
14. የአሮኖን ወንዝ እስራኤል ከእነርሱ ጋር የተዋጉትን አሞናውያን አጠፉ (ዘዳግ. ፪፡፳፭–፴፣)።
15. የናባ ተራራ ሙሴ የቃል ኪዳን ምድርን አየ (ዘዳግ. ፴፪፡፩–፬)። ሙሴ የመጨረሻ ሶስት ስብከቱን ሰበከ (ዘዳግ. ፩–፴፪)።
16. የሞአብ ሜዳ ጌታ ምድሩን እንዲከፋፈሉ እና በእዚያ የሚኖሩትን እንዲያጠፉ ነገራቸው (ዘኁል. ፴፫፡፶–፴፭)።
17. የዮርዳኖስ ወንዝ እስራኤል የዮርዳኖስን ወንዝ በደረቀ ምድር ላይ ተሻገሩ። በጌልገላ አጠገብ፣ ከዮርዳኖስ ወንዝ በታች የመጡ ድንጋዮች እንደ ዮርዳኖስ ወንዝ መከፈል ማስታወሻ ተቀመጡ (ኢያ. ፫፡፩–፭፡፩)።
18. ኢያሪኮ የእስራኤል ልጆች ከተማውን ያዙ እናም ደመሰሱ (ኢያ. ፮)።

3. የ፲፪ ነሳዎች መከፋፈል

4. የዳዊት እና የሰለሞን ግዛት



5. የአሶር ግዛት



6. አዲሱ የባቢሎን ግዛት (ናቡከደነፆር) እና የግብፅ ግዛት



7. የፋርሳዊ ግዛት



8. የሮሜ ግዛት

9. የብሉይ ኪዳን አለም



1. **አራራት ተራራ** በባህል የኖኅ መርከብ ያረፈበት ቦታ (ዘፍጥ. ፰፡፬)። እርግጠኛው ቦታ አይታወቅም።
2. **ውር** በኤፍራጥስ ወንዝ መጀመሪያ የሚገኝ የአብርሐም የመጀመሪያ መኖሪያ ቦታ፤ በእዚህም መስዋዕት ሊሆን ነበር፤ የያህዌ መልአክን አየ፤ እናም ኡሪም እና ቱሚምን ተቀበለ (ዘፍጥ. ፲፩፡፳፰–፲፪፡፩፤ አብር. ፩፡ ፫፡፩)። (ደግሞም በሰሜን መስጴጦምያ ውስጥ የሚገኘውን የውር ምትክ ቦታን ተመልከቱ።)
3. **ባቢሎን (ሰናዖር)** መጀመሪያ በካም ልጅ በኩሽ እና በናምሩድ የተሰፈረበት ቦታ። በሰናዖር ሚዳዎች ውስጥ በባቢሎን ማማ ዘመን ይሬዳውያን የመጡበት ቦታ። በጓላም የባቢሎን የክልል ዋና ከተማ እና የባቢሎን ንጉሶች፤ በተጨማሪም ኢየሩሳሌም ከተደመሰሰች በኋላ ብዙ አይሁዶችን በምርኮ ወደ ከተማዋ የወሰደው የናቡከደነፆር፤ መኖሪያ (፭፤፲፫፤፲፯ ም.ዓ.)። አይሁዶችን ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው ቤተመቅደስን እንዲገነቡ እስከፈቀደላቸው የንጉስ ቂሮስ ጊዜ ድረስ ለ፸ አመት አይሁዶች በምርኮ ቀሩ። ነቢዩ ዳንኤል ደግሞም በናቡከደነፆር፤ ብልጣሶር፤ እና በዳርዮስ ቀዳማዊ ስር ኖረ (ዘፍጥ. ፲፡፲፤ ፲፩፡፩–፱፤ ፪ ነገሥ. ፳፬፡፳፭፤ ኤር. ፳፯፡፩–፳፱፡፲፤ ሕዝ. ፩፡፩፤ ዳን. ፩–፲፪፤ ኦምኒ ፩፡፳፪፤ ኤተር ፩፡፴፣–፴፣)።
4. **ሱሳ** በዳርዮስ ቀዳማዊ (ታላቁ ዳርዮስ)፤ ዘርዘስ (አርጤክስስ)፤ እና አርጤክስስ ስር የፋርሳዊው ግዛት ዋና ከተማ ነበረች። በብርቱነቷ እና በእምነቷ የአይሁድ ህዝቦችን ያዳነችው የንግስት አስቴር መኖሪያም ነበር። ዳንኤል እናም በጓላም ነህምያ በእዚህ ቦታ አገለገሉ (ነህ. ፩፡ ፩፤ ፪፡ ፩፤ አስቴ. ፩፡ ፩፤ ዳን. ፰፡ ፪)።
5. **የዱራ ሜዳ** ሲድራት፣ ሚሳቅ፣ እና አብደናጎ በናቡከደነፆር የተሰራውን የወርቅ ምስልን ለማምለክ እምቢ ሲሉ ወደ እቶን እሳት ተጣሉ፤ የእግዚአብሔር ልጅ አዳናቸው፤ እናም ከእቶን እሳት ምንም ሳይጎዱ ወጡ (ዳን. ፫)።
6. **አሶር** አሦር በነነዌ የምትከተል የአሶር ዋና ከተማ። በ፯፻፳፭ ም.ዓ.፤ የአሶር ገዢዎች ስልምናሶር አምስተኛው እና ሳርጎን ሁለተኛው የእስራኤልን የሰሜን ግዛት አሸነፈ እናም አስር ነሳዎች በምርኮ ወሰዱ (፪ ነገሥ. ፲፯–፲፭፤ ፲፯–፲፱)። አሶር በባቢሎን እስከተሸነፈችበት እስከ ፮፻፲፪ ም.ዓ. ድረስ ይሁዳን ታስፈራራ ነበር።
7. **ነነዌ** የአሶር ዋና ከተማ። አሶር የይሁዳን ምድር በሕዝቅያስ ግዛት እና በነቢዩ ኢሳይያስ ጊዜ አጠቃች። የይሁዳ ዋና ከተማ መልአክ ፻፹፭ ሺህ የአሶር ወታደሮችን በመምታቱ ምክንያት የይሁዳ ዋና ከተማ ኢየሩሳሌም በተአምራት ዳነች (፪ ነገሥ. ፲፱፡ ፴፪–፴፮)። ጌታ ነቢዩ ዮናስን ይህችን ከተማ ንስሐ እንድትገባ እንዲጠራ ነገረው (ዮና. ፩፡፪፤ ፫፡ ፩–፬)።
8. **ሐራን** አብርሐም ወደ ከነዓን ከመሄዱ በፊት በእዚህ ቦታ ሰፈረ። የአብርሐም አባት እና ወንድም በእዚህ ቦታ ቀሩ። ርብቃ (የይስሐቅ ባለቤት)፣ ራሔል፣ ልያ፣ ባላ፣ እና ዘለፋ (የያዕቆብ ሚስቶች) ከእዚህ አካባቢ የመጡ ነበሩ (ዘፍጥ. ፲፩፡ ፴፩–፴፪፤ ፳፱፡ ፲፤ ፳፱፡ ፭–፮፤ አብር. ፪፡ ፭–፮)።
9. **ከርከሚሽ** በእዚህ ቦታ ፈርዖን ኒካው በናቡከደነፆር ተሸነፈ፤ ይህም በከነዓን የነበራትን የግብፅ ሀይል ፈጸመ (፪ ዜና ፴፭፡ ፳–፴፮፡ ፯)።
10. **ሲዶን** ይህ ከተማ የተመሰረተው በካም የልጅ ልጅ ሲዶን ነበር፤ እናም የከነዓን የደቡብ ከተማ ነው (ዘፍጥ. ፲፡ ፲፭–፳)። ይህም ወደ እስራኤል በአልን ማምለክ ያስተዋወቀችው የኤልዛቤል ቤት ነበር (፩ ነገሥ. ፲፮፡ ፴–፴፣)።
11. **ጢሮስ** ይህችም በአሶር ውስጥ አስፈላጊ የንግድ እና የባህር ወደብ ከተማ ነበረች። የጢሮስ ኪራም እንጨት እና ወርቅ እንዲሁም ባለሚተኞች ሰለሞንን ቤተመቅደሱን ሲሰራ እንዲረዱት ላከ (፩ ነገሥ. ፭፡ ፩–፣፡ ፣፣፡ ፣፡ ፣፩)።
12. **ደማስቆ** አብርሐም ሎጥን ከእዚህ ቦታ አጠገብ አዳነው። ይህችም የአሶር ዋና ከተማ ነበረች። በንጉስ ዳዊት ዘመነ መንግስት፣ እስራኤላውያን ይህችን ከተማ አሸነፉ። ኤልያስ አዛዥል የደማስቆ ንጉስ እንዲሆን ቀባው (ዘፍጥ. ፲፬፡ ፲፬–፲፭፤ ፪ ሳሙ. ፰፡ ፭–፮፤ ፩ ነገሥ. ፲፱፡ ፲፭)።
13. **ከነዓን** አብርሐም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብ፣ እናትውልዶቻቸው ይህን ምድር እንደ ዘለአለማዊ ውርስ ተሰጣቸው (ዘፍጥ. ፲፯፡ ፰፣ ፳፰፡)።
14. **የሲና ተራራ** (ኮሬብ) ጌታ ሙሴ በሚነድ ቍጥቋጦ አነጋገረው (ዘፀአ. ፫፡ ፩–፪)። ሙሴ ህግ እና አስርቱ ቃላት ተሰጥተውት ነበር (ዘፀአ. ፲፱–፳)። ጌታ ከኤልያስ ጋር በትንሽ የዝምታ ድምፅ አነጋገረው (፩ ነገሥ. ፲፱፡ ፭–፲፪)።
15. **ዔጽዮንጋብር** ንጉስ ሰለሞን በዔጽዮንጋብር "የባህር ሀይል መርከብ" ገንብቶ ነበር (፩ ነገሥ. ፱፡ ፳፮)። ምናልባት የሰለሞንን ታዋቂነት ከሰማች በኋላ የሳባ ንግስት የመጣችው በእዚህ የባህር ወደብ ላይ ነው (፩ ነገሥ. ፣፡ ፩–፣፣)።
16. **ግብፅ** አብርሐም በውር በነበረው ታላቅ ርሀብ ምክንያት ወደ እዚህ ተጓዘ (አብር. ፪፡ ፩፤ ፳፩)። ጌታ አብርሐምን ለግብጾች እርሱ የገለጸለትን እንዲያስተምር ነገረው (አብር. ፫፡ ፣፩)። የዮሴፍ ወንድሞች ወደ ባርነት ከሸጡት በኋላ (ዘፍጥ. ፴፯፡ ፳፰)፣ ዮሴፍ በእዚህ ቦታ የጲጥፋራ ቤት ገዢ ሆነ። ወደ እስር ቤት ተጣለ። የፈርዖን ህልም ተረጎመ እናም በግብፅ ውስጥ የስልጣን ሀላፊነት ተሰጠው። ዮሴፍ እና ወንድሞቹ እንደገና ተገናኙ። ያዕቆብ እና ቤተሰቡ ወደ እዚህ መጡ (ዘፍጥ. ፴፱–፴፯)። የእስራኤል ልጆች በግብፅ በቆዩበት ጊዜ በጌሣም ውስጥ ይኖሩ ነበር (ዘፍጥ. ፴፯፡ ፣)።

    እስራኤላውያን ተባዙ "እናም አጅግም ጸኑ"፤ ከእዚያም በኋላ ግብጻዊያን ባሪያዎች እንዲሆኑ አደረጓቸው (ዘፀአ. ፩፡ ፣–፣፡)። ከብዙ ወረርሽኝ በኋላ ፈሮኦኑ እስራኤል ከግብጽ እንዲወጡ ፈቀደላቸው (ዘፀአ. ፲፪፡ ፴፩–፴፩)። ኤርምያስ ወደ ግብጽ ተወሰደ (ኤር. ፴፣፡ ፡–፣)።
17. **ከፍቶር** (ቀርጤስ) የጥንት የሚኖዓን ምድር ነበር።

10. ከነዓን በብሉይ ኪዳን ዘመናት

1. ዳን (ሌሳ) ኢዮርብዓም የሰሜን መንግስት እንዲያመልኩት የወርቅ ጥጃ ሰራላቸው (፩ ነገሥ. ፲፪፡ ፳፯–፴፫)። ዳን የጥንት እስራኤል የሰሜን ገደብ ነው።
2. ቀርሜሎስ ተራራ ኤልያስ ከበኣል ካህናት ጋር ተፎካከረ እናም ሰማያትን ለዝናብ ከፈተ (፩ ነገሥ. ፲፰ ፡ ፲–፴፮)።
3. መጊዶ ብዙ ጦርነት የተዋጉበት ቦታ (መሳ. ፬ ፡ ፲፫–፲፯፣ ፭ ፡ ፲፱፣ ፪ ነገሥ. ፳፫ ፡ ፳፱፣ ፪ ዜና ፴፭ ፡ ፳–፳፫)። ሰለሞን መጊዶ ለመገንባት ቀረጥ መደበ (፩ ነገሥ. ፱ ፡ ፲፭)። የይሁዳ ንጉስ ኢዮስያስ ከግብፅ ፈሮዖን ኒካው ጋር በተዋጋበት ጊዜ ቆስሎ ሞተ (፪ ነገሥ. ፳፫ ፡ ፳፱–፴)። በጌታ ዳግም ምፅዓት፣ እንደ አርማጌዶን ጦርነት ክፍል በኢዝራኤል ሸለቆ ታላቅ ጦርነት ይኖራል (ኢዩ. ፫ ፡ ፲፬፣ ራዕ. ፲፮ ፡ ፲፮፣ ፲፱ ፡ ፲፩–፳፩)። አርማጌዶን የሚባለው ስም በግሪክ ቋንቋ የተተረጎመ የዕብራውያን ሀር መጊዶ፣ ወይም የመጊዶ ተራራ ስም ነው።
4. ኢይዝራኤል ከሁሉም በላይ የለማ የእስራኤል ሸለቆ ጋር አንድ አይነት ስም ያለው እና ከሁሉም ታላቅ ከተማ ስም። የሰሜን መንግስት ንጉሶች በእዚህ ቦታ ቤተመንግስት ሰሩ (፪ ሳሙ. ፪ ፡ ፳–፴፣ ፭ ነገሥ. ፳፭ ፡ ፭–፪)። ክፉ የነበረችው ንግስት ኤልዛቤል በእዚህ ቦታ ኖረች እናም ሞተች (፩ ነገሥ. ፳፩ ፣ ፪ ነገሥ. ፱ ፡ ፴)።
5. ቤትሳን እስራኤል ከነዓናውያንን በእዚህ ቦታ ተቋቋመች (ኢያ. ፲፯ ፡ ፲፪–፲፮)። የሳኦል ሰውነት በእዚህ ምሽግ ግድግዳ ላይ ታስሮ ነበር (፩ ሳሙ. ፴፩ ፡ ፲–፲፫)።
6. ዶታይን ዮሴፍ በወንድሞቹ ወደ ባሪያነት ተሸጠ (ዘፍጥ. ፴፯ ፡ ፲፯፣ ፳፰ ፣ ፴፭ ፡ ፭)። ኤልሳዕ በፈረሶች እና በሰረገላ የተሞላ ተራራ ራዕይ አየ (፪ ነገሥ. ፮ ፡ ፲፪–፲፯)።
7. ሰማርያ የሰሜን መንግስት ዋና ከተማ (፩ ነገሥ. ፲፮ ፡ ፳፬–፳፱)። ንጉስ አሀብ የበኣል ቤተመቅደስ ሰራ (፩ ነገሥ. ፲፮ ፡ ፴፪–፴፫)። ኤልያስ እና ኤልሳዕ አገለገሉ (፩ ነገሥ. ፲፰ ፡ ፪፣ ፪ ነገሥ. ፮ ፡ ፲፱–፳)። በ፯፻፳፭ ም.ዓ. አሶር የአስር ጎሳዎች መያዝን በመፈጸም አሸነፈቻት (፪ ነገሥ. ፲፰ ፡ ፱–፲)።
8. ሴኬም አብርሐም መሰዊያ ገነባ (ዘፍጥ. ፲፪ ፡ ፮–፯)። ያዕቆብ በእዚህ ቦታ አጠገብ ኖረ። ስምዖን እና ሌዊ የከተማዋን ወንዶች በሙሉ ገደሉ (ዘፍጥ. ፴፬ ፡ ፳፭)። ኢያሱ "በእዚህ ቀን" እግዚአብሔርን ለማገልገል "ምረጡ" ያለበት ማበረታቻ የነበረው በሴኬም ነበር (ኢያ. ፳፬ ፡ ፲–፳)። ኢዮርብዓም የሰሜን መንግስት የመጀመሪያውን ከተማ በእዚህ ቦታ መሰረተ (፩ ነገሥ. ፲፪)።
9. ጌባል ተራራ እና ገሪዛን ተራራ ኢያሱ እስራኤልን በእነዚህ ሁለት ተራራዎች ላይ ከፋፈላቸው—የህጉ በረከቶች ከገሪዛ ተራራ ታወጀ፣ እርግማኑም ከጌልባ ተራራ መጣ (ኢያ. ፰ ፡ ፴፫)። ሳምራዊዎች በኋላም በገሪዛ ላይ ቤተመቅደስ ገነቡ (፪ ነገሥ. ፲፯ ፡ ፴፪–፴፫)።
10. ፓኒኤል ያዕቆብ ከጌታ መልእክተኛ ጋር በምሽት በሙሉ ታገለ (ዘፍጥ. ፴፪ ፡ ፳፬–፴፪)። ጌዴዎን የም ድያማውያን ምሽግን ደመሰሰ (መሳ. ፰ ፡ ፭ ፣ ፰–፱)።
11. ኢዮጴ ዮናስ የነነዌ ሚስዮኑን ለማስወገድ ከእዚህ ቦታ ወደ ተርሴስ በመርከብ ተጓዘ (ዮና. ፩ ፡ ፩–፫)።
12. ሴሎ በመሳፍንት ዘመን፣ የእስራኤል ዋና ከተማ እና ታቦቱ ይገኝበት የነበረ ቦታ (፩ ሳሙ. ፬ ፡ ፫–፬)።
13. ቤቴል (ሎዛ) በእዚህ ቦታ አብርሐም ከሎጥ ጋር ተለያየ (ዘፍጥ. ፲፫ ፡ ፩–፲፩) እናም ራዕይ አየ (ዘፍጥ. ፲፫ ፣ አብር. ፪ ፡ ፲፱–፳)። ያዕቆብ ወደሰማይ የሚደርስ መሰላል ራዕይ አየ (ዘፍጥ. ፳፰ ፡ ፲–፳፪)። ለጊዜም ታቦት በእዚህ ቦታ ይገኝ ነበር (መሳ. ፳ ፡ ፳፯–፳፰)። ኢዮርብዓም የሰሜን መንግስት እንዲያመልኩት የወርቅ ጥጃ ሰራላቸው (፩ ነገሥ. ፲፪ ፡ ፳፯–፴፫)።
14. ገባዖን ኬጢያውያን ኢያሱን በማታለል ስምምነት እንዲገባ አደረገ (ኢያ. ፱)። ኢያሱ ጦርነትን እያሸነፈ እያለ ፀሐይም በሰማይ መካከል ዘገየ (ኢያ. ፣ ፡ ፪–፲፫)። ይህም የታቦት ለጊዜ የሚቀመጥበት ቦታ ነበር (፩ ዜና ፲፮ ፡ ፴፱)።
15. ጋዛ፣ አዛጦን፣ አስቀሎና፣ አቃሮን፣ ጌት (የፍልስጥኤማውያን አምስት ከተማዎች) በብዙ ጊዜ ፍልስጥኤማውያን ከእነዚህ ከተማዎች እስራኤልን ያጠቁ ነበር።
16. ቤተ ልሔም ራሔል በእዚህ ቅርብ ነበር የተቀበረችው (ዘፍጥ. ፴፭ ፡ ፲፱)። ሩት እና ቦዓዝ በእዚህ ኖሩ (ሩት ፩ ፡ ፩–፪ ፣ ፪ ፡ ፩ ፣ ፬)። ይህም የዳዊት ከተማ ነበር (ሉቃ. ፪ ፡ ፬)።
17. ኬብሮን አብርሐም (ዘፍጥ. ፲፫ ፡ ፲፰)፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብ (ዘፍጥ. ፴፭ ፡ ፳፯)፣ ዳዊት (፪ ሳሙ. ፪ ፡ ፩–፬)፣ እና አቤሴሎም (፪ ሳሙ. ፲፭ ፡ ፣) በእዚህ ኖሩ። ይህ በንጉስ ዳዊት ስር የይሁዳ የመጀመሪያ ዋና ከተማ ነበር (፪ ሳሙ. ፪ ፡ ፲፩)። አብርሐም፣ ሳራ፣ ይስሐቅ፣ ርብቃ፣ ያዕቆብ፣ እና ልያ በእርሻ ባለ ድርብ ክፍል ዋሻ ውስጥ ተቀብረዋል ተብሎ ይታመናል (ዘፍጥ. ፳፫ ፡ ፲፯–፳ ፣ ፴፱ ፡ ፴፩፣ ፴፱ ፣ ፴፫)።
18. ዓይንጋዲ ዳዊት ከሳያል ተደበቀ እናም የሳያልን ህይወት አተረፈ (፩ ሳሙ. ፳፫ ፡ ፳፱–፳፬ ፡ ፳፪)።
19. ጌራራ አብርሐም እና ይስሐቅ ለጊዜ በእዚህ ቦታ ይኖሩ ነበር (ዘፍጥ. ፳ –፳፪ ፣ ፳፮)።
20. ቤርሳቤህ አብርሐም በእዚህ ቦታ የውሀ ጉድጓድ ቆፈረ እናም ከአቢሜሌክ ጋር ቃል ኪዳን ገባ (ዘፍጥ. ፳፩ ፡ ፴፩)። ይስሐቅ ጌታን አየ (ዘፍጥ. ፳፮ ፡ ፲፯ ፣ ፳፫–፳፭)፣ እናም ያዕቆብ በእዚህ ቦታ ይኖር ነበር (ዘፍጥ. ፴፭ ፡ ፲ ፣ ፴፮ ፡ ፩)።
21. ሰዶም እና ገሞራ ሎጥ በሰዶም ለመኖር መረጠ (ዘፍጥ. ፲፫ ፡ ፲፩–፲፪ ፣ ፲፱ ፡ ፲፪)። እግዚአብሔር ሰዶም እና ገሞራን በኃጢያተኛነት ምክንያት ደመሰሰ (ዘፍጥ. ፲፱ ፡ ፳፬–፳፮)። በኋላም ኢየሱስ እነዚህን ከተማዎች እንደ ኃጢያተኛነት ምሳሌዎች ተጠቀመባቸው (ማቴ. ፲ ፡ ፲፭)።

11. ቅዱስ ምድር በአዲስ ኪዳን ዘመናት

1. ጢሮስ እና ሲዶን ኢየሱስ ኮራዚና ቤተ ሳይዳን ከጢሮስ እና ሲዶን ጋር አነጻጸረ (ማቴ. ፲፩፡ ፳–፳፪)። የአህዛብ ሴትን ሴት ልጅን ፈወሰ (ማቴ. ፲፭፡ ፳፩–፳፰)።
2. የመለወጫ ተራራ ኢየሱስ በጴጥሮስ፣ ያዕቆብ፣ እና ዮሐንስ ፊት ተለወጠ፣ እና እነርሱም የመንግስት ቁልፎችን ተቀበሉ (ማቴ. ፲፮፡ ፩–፲፮)። (አንዳንዶች የመለወጫ ተራራ አርሞንዔም ተራራ ነው ብለው ያምናሉ፤ ሌሎችም የታቦር ተራራ ነው ብለው ያምናሉ)።
3. ፊልጵስ ቂጣሮያ ጴጥሮስ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እን ደሆነ መሰከረ እናም የመንግስት ቁልፎችንም ቃል ተገባለት (ማቴ. ፲፮፡ ፲፫–፳)። ኢየሱስ የእራሱን ሞት እና ትንሳኤ አስቀድሞ ተናገረ (ማቴ. ፲፮፡ ፳፩–፳፳)።
4. የገሊላ ክልል ኢየሱስ አብዛኛውን ህይወቱን እና አገ ልግሎቱን በገሊላ አሳለፈ (ማቴ. ፬፡ ፳፫–፳፭)። በእ ዚህም የተራራ ስብከትን ሰጠ (ማቴ. ፭–፯)፤ ለምጻ ሞችን ፈወሰ (ማቴ. ፰፡ ፩–፬)፤ እናም አስራ ሁለት ሐዋሪያትን መረጠ፣ ወይም ሾመ፣ እናም ላከ፣ ከእነ ርሱም መካከል የአስቆሮቱ ይሁዳ ከገሊላ የመጣ አል ነበረም (ማር. ፫፡ ፲፫–፲፱)። በገሊላ ውስጥ ከሞት የተ ነሳው ክርስቶስ በሐዋሪያት ታየ (ማቴ. ፳፰፡ ፲፯–፳)።
5. የገሊላ ባህር በጓላም የጥብርያዶስ ባህር ተብሎ የተጠራው፡ ኢየሱስ ከጴጥሮስ ጀልባ አስተማረ (ሉቃ. ፭፡ ፩–፣)፣ እናም ጴጥሮስን፣ እንድርያስን፣ ያዕቆብን የሰው አጥማጆች እንዲሆኑ ጠራቸው (ማቴ. ፬፡ ፲፰–፳፪፤ ሉቃ. ፭፡ ፩–፲፩)። አውሎ ንፋስንም ጸጥ አስደረገ (ሉቃ. ፰፡ ፳፪–፳፭)፣ ምሳሌዎችን ከጀልባ አስተማረ (ማቴ. ፲፣)፣ በባህር ላይ ተራመደ (ማቴ. ፲፬፡ ፳፪–፴፪)፣ እናም ከትንሳኤም በኋላ በደቀመዛ ሙርቱ ታየ (ዮሐ. ፳፩)።
6. ቤተ ሳይዳ ጴጥሮስ፣ እንድርያስ፣ እና ፊልጵስ በቤተ ሳይዳ ውስጥ ተወልደው ነበር (ዮሐ. ፩፡ ፵፬)። በቤተ ሳይዳ አጠገብ ኢየሱስ ከሐዋሪያት ጋር በሚስጥር ሄደ። ህዝብም ተከተሉት፣ እና ፭ ሺህን መገበ (ሉቃ. ፱፡ ፣–፲፯፤ ዮሐ. ፮፡ ፩–፲፬)። በእዚህም ቦታ ኢየሱስ አይነ ስውር ሰውን ፈወሰ (ማር. ፰፡ ፳፪–፳፮)።
7. ቅፍርናሆም ይህም የጴጥሮስ ቤት ነበር (ማቴ. ፰፡ ፭፣ ፣ ፣ ፲፬)። ማቴዎስ የኢየሱስ “የእርሱ ከተማ” ብሎ በጠራው በቅፍርናሆም፣ ኢየሱስ ሽባ የሆነውን ሰው ፈወሰ (ማቴ. ፱፡ ፩–፣)፤ ማር. ፪፡ ፩–፲፪)፣ የአ ስር አለቃን አዳነ፣ የጴጥሮስ ሚስት እናትን ፈወሰ (ማቴ. ፰፡ ፭–፲፭)፣ ማቴዎስ ከሐዋሪያቱ መካከል አንዱ እንዲሆን ጠራው (ማቴ. ፱፡ ፱)፣ አይነ ስውር አይኖችን ከፈተ፣ ዲያቦስን አስወጣ (ማቴ. ፱፡ ፳፯–፴፫)፣ እጁ የሰለለች ሰውን በሰንበት ፈወሰ (ማቴ. ፲፪፡ ፱–፲፫)፣ የህይወት እንጀራ ስብከትን ሰጠ (ዮሐ. ፮፡ ፳፪–፴፭)፣ እና ጴጥሮስን ከአሳ አፍ ገንዘብ እን ዲያመጣ በመንገር፣ ቀረጥን ለመክፈል ፈቃደኛ ሆነ (ማቴ. ፲፯፡ ፳፩–፳፯)።
8. መጌዶል ይህም የመጌዶል ማርያም ቤት ነበር (ማር. ፲፮፡ ፱)። ኢየሱስ ፱ ሺህ ህዝቦችን ከመገበ በኋላ ወደ እዚህ መጣ (ማቴ. ፲፭፡ ፴፪–፴፱)፣ እናም ፈሪሳዊ እና ሰዱቃውያን ከሰማይ ምልክት እንዲያሳያቸው ጠየቁ (ማቴ. ፲፮፡ ፩–፬)።
9. ቃና ኢየሱስ ውሀን ወደ ወይን ቀየረ (ዮሐ. ፪፡ ፩–፲፩) እና በቅፍርናሆም የነበረን የልውል ሰው ልጅን ፈወሰ (ዮሐ. ፬፡ ፵፯–፶፬)። ቃና የናትናኤል ቤት ነበር (ዮሐ. ፳፩፡ ፪)።
10. ናዝሬት ለማርያም እና ለዮሴፍ የተሰጠው ብስራት የነበረው በእዚህ ቦታ ነበር (ማቴ. ፩፡ ፲፰–፳፭፤ ሉቃ. ፩፡ ፳፮–፴፰፣ ፪፡ ፬–፭)። ከግብፅ ከተመለሱ በኋላ፣ ኢየሱስ ልጅነቱን እና ወጣትነቱን በዚህ ቦታ አሳለፈ (ማቴ. ፪፡ ፲፱–፳፫፣ ሉቃ. ፪፡ ፣፩–፣፪)፣ መሲህ እንደ ሆነ አስታወቀ፣ እናም በእርሱ ሰዎች ተወገደ (ሉቃ. ፬፡ ፲፰–፴፪)።
11. ኢያሪኮ ኢየሱስ ለአይነ ስውር ሰው እይታን ሰጠ (ሉቃ. ፲፰፡ ፴፭–፴፫)። ከቀራጮች መካካል ዋና ከሆ ነው ከዘካርያስ ጋር በላ (ሉቃ. ፲፱፡ ፩–፣)።
12. ቤተ ራባ መጥምቁ ዮሐንስ “በምድረ በዳ የሚጮህ ሰው ድምፅ” እንደሆነ መሰከረ (ዮሐ. ፩፡ ፲፱–፳፰)። ዮሐንስ ኢየሱስን በዮርዳኖስ ወንዝ አጠመቀ እናም ኢየሱስ የእግዚአብሔር በግ እንደሆነ መሰከረ (ዮሐ. ፩፡ ፳፱–፴፬)።
13. የይሁዳ ምድረበዳ መጥምቁ ዮሐንስ በምድረበዳ ሰበከ (ማቴ. ፣፡ ፩–፬)፣ በእዚህም ኢየሱስ ለአርባ ቀናት ጾመ እናም ተፈተነ (ማቴ. ፬፡ ፩–፲፩)።
14. ኤማሁስ ከሞት የተነሳው ክርስቶስ በኤማሁስ መን ገድ ላይ ከሁለቱ ደቀመዛሙርቱ ጋር ሄደ (ሉቃ. ፳፬፡ ፣፣–፴፪)።
15. ቤተ ፋጌ ሁለት ደቀመዛሙርት ለኢየሱስ ውርን ጫይቱን አመጡለት በዚህም ላይ ወደ ኢየሩሳሌም በድል ገባ (ማቴ. ፳፩፡ ፩–፲፩)።
16. ቢታንያ ይህ የማርያም፣ የማርታ፣ እና የአልዓዛር ቤት ነበር (ዮሐ. ፲፩፡ ፩)። ማርያም የኢየሱስን ቃላት ሰማች፣ እናም ኢየሱስ ማርታን “መልካሙን እድ ልን” ስለመምረጥ ተናገረ (ሉቃ. ፣፡ ፴፰–፴፪)፣ ኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት አስነሳው (ዮሐ. ፲፩፡ ፩–፴፪)፣ እናም ማርያም የኢየሱስን እግር ቀባች (ማቴ. ፳፮፡ ፮–፣፣፣ ዮሐ. ፲፪፡ ፩–፳)።
17. ቤተ ልሔም ኢየሱስ ተወልዶ በግርግም ውስጥ ተኛ (ሉቃ. ፪፡ ፩–፯)፣ መላእክት ለእረኞች የኢየ ሱስ መወለድን አወጁ (ሉቃ. ፪፡ ፰–፳)፣ ሰብእ ሰገል በኢየሱስ ኮከብ ተመርተው ነበር (ማቴ. ፪፡ ፩–፲፪)፣ እናም ሂሮድስ ልጆችን ገደለ (ማቴ. ፪፡ ፲፯–፲፰)።

12. ኢየሩሳሌም በኢየሱስ ጊዜ



1. **ጎልጎታ** የኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት ሊሆን የሚ ችል ቦታ (ማቴ. ፳፯፡ ፴፫–፴፯)።
2. **የአትክልት ስፍራ መቃብር** የኢየሱስ ሰውነት ያረፈ በት ሊሆን የሚችል አንድ ቦታ (ዮሐ. ፲፱፡ ፴፰–፴፪)። ከሞት የተነሳው ኢየሱስ ለመግደላዊ ማርያም በመቃ ብሩ ውጪ በሚገኘው የአትክልት ስፍራ ውስጥ ታየ (ዮሐ. ፳፡ ፩–፲፣)።
3. **የአንቶኒያ ምሽግ** ኢየሱስ የተከሰሰበት፣ ተፈረደበት፣ ተሰደበበት፣ እና የተገረፈበት በእዚህ ቦታ ላይ ይሆናል (ዮሐ. ፲፰፡ ፳፫–፲፱፡ ፲፮)። ጳውሎስ ታሰረ እናም የተ ቀየረበትን ታሪክ ነገረ (የሐዋ. ፳፭፡ ፴፩–፳፪፡ ፳፭)።
4. **የቤተ ሳይዳ መጠመቂያ** ገናዳ ኢየሱስ ሽባን ሰው በሰ ንበት ፈወሰ (ዮሐ. ፭፡ ፪–፱)።
5. **ቤተመቅደስ** ገብርኤል ለዘካርያስ ኤልሳቤጥ ወንድ ልጅ እንደምትወልድ ነገረው (ሉቃ. ፩፡ ፭–፳፭)። የቤ ተመቅደስ መጋረጃ በአዳኝ ሞት ጊዜ ተቀደደ (ማቴ. ፳፯፮፡ ፶፩)።
6. **የሰለሞን ሰቀላ** ኢየሱስ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አወጀ። አይሁዶች ኢየሱስን ለመውገር ሞከሩ (ዮሐ. ፣፡ ፳፪–፳፱)። ጴጥሮስ አንካሳ ሰውን ከፈወሰ በኋላ ንስሀ መግባትን ሰበከ (የሐዋ. ፫፡ ፲፩–፳፯)።
7. **መልካም ደጅ** ጴጥሮስ እና ዮሐንስ አንካሳ ሰው ፈወሱ (የሐዋ. ፫፡ ፩–፣)።
8. **የቤተመቅደስ ጫፍ** ኢየሱስ በሰይጣን ተፈተነ (ማቴ. ፬፡ ፭–፯) (ይህ ድርጊት ሊደርስ የቻለበት ቦታ።)
9. **ቅዱስ ተራራ** (የማይታወቅ ቦታ)
   ሀ. በባህል አብርሐም ይስሐቅን የሚሰዋበት መሰዊያ በእዚህ ቦታ ገነባ ይባላል (ዘፍጥ. ፳፪፡ ፱–፲፬)።
   ለ. ሰለሞን ቤተመቅደስን ገነባ (፩ ነገሥ. ፮፡ ፩–፣፡ ፪ ዜና ፡፡ ፡ ፩)።
   ሐ. ባቢሎን ቤተመቅደሱን በ፭፻፹፯ ም.ዓ. ደመሰሱት (፪ ነገሥ. ፳፭፡ ፡–፱)።
   መ. ዘሩባቤል ቤተመቅደስን በ፭፻፲፭ ም.ዓ. እንደገና ገነባ (ዕዝ. ፫፡ ፡–፣፡ ፭ ፡ ፪፡ ፣ ፮፡ ፣–፣፯)።
   ሠ. ሄሮድስ የቤተመቅደስ አደባባይን አስፋፋ እናም በ፣፲፯ ም.ዓ. ቤተመቅደስን እንደገና መገንባት ጀመረ። ኢየሱስ በህጻንነቱ በእዚህ ቀረበ (ሉቃ. ፪፡ ፳፪–፴፱)።
   ረ. በ፣፲፪ አመቱ ኢየሱስ በቤተመቅደስ አስተማረ (ሉቃ. ፪፡ ፵፮–፶)።
   ሰ. ኢየሱስ ቤተመቅደስን አጸዳ (ማቴ. ፳፩፡ ፣፪–፣፮፡ ዮሐ. ፪፡ ፣፣–፣፯)።
   ሸ. ኢየሱስ በተለያዩ ጊዜዎች በቤተመቅደስ አስተማረ (ማቴ. ፳፩፡ ፳፣–፳፣፡ ፴፱፣ ዮሐ. ፯፡ ፣፡–፡ ፡ ፶፱)።
   ቀ. በቲቶ ስር ሮሜዎች ቤተመቅደስን በ፷ ዓ.ም. ደመ ሰሱ።
10. **ጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ** ኢየሱስ ተሰቃየ፣ ተካደ፣ እናም ታሰረ (ማቴ. ፳፮፡ ፴፯–፶፮፡ ሉቃ. ፳፪፡ ፴፱–፶፪)።
11. **ደብረ ዘይት ተራራ**
   ሀ. ኢየሱስ የኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ መደምሰስን አስ ቀድሞ ነገረ። ስለዳግም ምፅዓት ደግሞም ተናገረ (ማቴ. ፳፬፡ ፣–፳፭፡ ፶፯፣ ደግሞም ፲. ስ.—ማቴ ተመልከቱ)።
   ለ. ከእዚህ ቦታ ኢየሱስ ወደ ሰማይ አረገ (የሐዋ. ፩፡ ፱–፲፪)።
   ሐ. በጥቅምት ፳፬ ቀን ፣፲፱፻፶፩ (እ.አ.አ.)፣ ሽማግሌው አርሰን ሀይድ ቅዱስ ምድርን ለአብርሐም ልጆች በዳግም መመለስ ቀደሰ።
12. **የግዮን ምንጭ** ሰለሞን እንደንጉስ ተቀባ (፩ ነገሥ. ፩፡ ፴፰–፴፱)። ሕዝቅያስ ከምንጩ ወደ ከተማው ውሀ ለማምጣት መንገድ አስቆፈረ (፪ ዜና ፴፪፡ ፴)።
13. **የውኃው በር** ዕዝራ የሙሴን ህግ ለህዝቡ አነበበ እናም ተረጎመ (ነህ. ፰፡ ፩–፰)።
14. **ሄኖም ሸለቆ** ልጅ ከመሰዋት በተጨማሪ የሀሰት ጣዖት ሞሎክ አመለኩት (፪ ነገሥ. ፳፫፡ ፣፣ ፪ ዜና ፳፰፡ ፣)።
15. **የቀያፋ ቤት** ኢየሱስ በቀያፋ ቤት ተወሰደ (ማቴ. ፳፮፡ ፶፯–፷፰)። ጴጥሮስ ኢየሱስን ያውቅ እንደነበረ ካደ (ማቴ. ፳፮፡ ፷፱–፸፭)።
16. **ታላቅ አዳራሽ** በባህል ይህ ኢየሱስ የፋሲካ ምግብን የበ ላበት እና ቅዱስ ቁርባንን የጀመረበት ቦታ ነው (ማቴ. ፳፮፡ ፣፰–፴)። የሐዋሪያትን እግሮች አጠበ (ዮሐ. ፣፣፡ ፡–፣፣)፣ እናም አስተማራቸው (ዮሐ. ፣፣፡ ፣፣–፣፮፡ ፣፰፮)።
17. **የሄሮድስ ቤተመንግስት** ክርስቶስ በሄሮድስ ፊት ቀረበ፣ ምናልባት በእዚህ ቦታ (ሉቃ. ፳፣፡ ፣–፣፩)።
18. **ኢየሩሳሌም** (የማይታወቅ ቦታ)
   ሀ. መልከ ጼዴቅ እንደ ሳሌም ንጉስ ገዛ (ዘፍጥ. ፣፬፡ ፣፣)።
   ለ. ንጉስ ዳዊት የኢያቡሳውያን ከተማን አሸነፈ (፪ ሳሙ. ፭፡ ፣፣፣ ፩ ዜና ፣፩፡ ፡–፣)።
   ሐ. በ፭፻፹፯ ም.ዓ. ከተማው በባቢሎን ተደመሰሰ (፪ ነገሥ. ፳፭፡ ፩–፣፩)።
   መ. በበዓለ ኀምሳ ቀን መንፈስ ቅዱስ ብዙዎችን ሞላ (የሐዋ. ፪፡ ፩–፱)።
   ሠ. ጴጥሮስ እና ዮሐንስ ታሰሩ እናም በሸንጎዎች ፊት ቀረቡ (የሐዋ. ፬፡ ፩–፳፣)።
   ረ. ሐናንያ እና ሰጲራ ለጌታ ዋሹ እናም ሞቱ (የሐዋ. ፭፡ ፩–፣)።
   ሰ. ጴጥሮስ እና ዮሐንስ ታሰሩ፣ ነገር ግን መልአክ ከእ ስር ቤት አዳናቸው (የሐዋ. ፭፡ ፣፣–፳)።
   ሸ. ሐዋሪያት ሰባት ሰዎች እንዲረዷቸው መረጡ (የሐዋ. ፮፡ ፩–፮)።
   ቀ. የእስጢፋኖስን ምስክርን አይሁዶች አስወገዱ፣ እናም እስኪሞት ድረስ ተወገረ (የሐዋ. ፮፡ ፰–፯፡ ፰)።
   በ. ያዕቆብ ሰማዕት ሆነ (የሐዋ. ፣፪፡ ፩–፪)።
   ተ. መልአክ ጴጥሮስን ከእስር ቤት አወጣው (የሐዋ. ፣፪፡ ፭–፣፩)።
   ቸ. ሐዋሪያት የግርዘት ጉዳይን ወሰኑ (የሐዋ. ፣፭፡ ፭–፳፱)።
   ኀ. በቲቶ ስር ሮሜዎች ቤተመቅደስን በ፷ ዓ.ም. ደመ ሰሱ።

13. የሐዋርያው ጳውሎስ የሚስዮን ጉዞ



1. ጋዛ ፊልጵስ ወደ ጋዛ ሲጓዝ ስለክርስቶስ ሰበከ እናም ኢትዮጵያዊ ጃንደረባን አጠመቀ (የሐዋ. ፰፡ ፳፮–፴፱)።
2. ኢየሩሳሌም በኢየሩሳሌም ስለነበሩት ድርጊቶች ካርታ 12ን ተመልከቱ።
3. ኢዮጴ ጴጥሮስ እግዚአብሔር ለአህዛቦች ንስሀ የመግባት ስጦታን እንደሰጠ ራዕይ ተቀበለ (የሐዋ. ፲፡ ፲፩፡፭–፲፰)። ጴጥሮስ ጣቢታን ከሞት አስነሳ (የሐዋ. ፱፡ ፴፮–፴፱)።
4. ሰማርያ ፊልጵስ በሰማርያ ውስጥ ሰበከ (የሐዋ. ፰፡ ፭–፲፫)፣ እናም ጴጥሮስ እና ዮሐንስ በኋላም በእዚህ ቦታ አስተማሩ (የሐዋ. ፰፡ ፲፡–፳፭)። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ከሰጡ በኋላ፣ አስማተኛው ስምዖን ይህን ስጦታ ከእነርሱ ለመግዛት ፈለገ (የሐዋ. ፰፡ ፱–፳፪)።
5. ቂሣሪያ መልእክ ለመቶ አለቃው ቆርኔሌዎስ ካገለገለ በኋላ፣ ጴጥሮስ እንዲጠመቅ ፈቀደለት (የሐዋ. ፣)። በእዚህ ቦታ ጳውሎስ በአግሪጳ ፊት ተከራከረ (የሐዋ. ፳፭–፳፮፣ ደግሞም ፳.ስ.—ታ. ፩፡ ፳፱–፳፭)።
6. ደማስቆ ኢየሱስ ለሳዖል ታየ (የሐዋ. ፱፡ ፩–፯)። ሐናንያ ሳዖል ለማየት እንዲችል ካደረገ በኋላ፣ ሳዖል ተጠመቀ እናም አገ ልግሎቱን ጀመረ (የሐዋ. ፱፡ ፣–፳፯)።
7. አንጾኪያ (በአሶር ውስጥ) በእዚህ ቦታ ደቀመዛሙርት ለመ ጀመሪያ ጊዜ ክርስቲያን ተብለው ተጠሩ (የሐዋ. ፲፩፡ ፳፮)። አጋቦስ ስለርዓብ ተነበየ (የሐዋ. ፲፩፡ ፳፯–፳፰)። በአንጾኪያ ስለግርዘት በሚመለከት ጥል ተጀመረ (የሐዋ. ፲፡ ፳፯–፳፰፣ ፲፭፡ ፩–፱)። በአንጾኪያ ጳውሎስ ከሲላስ፣ በርናባስ፣ እና ይሁዳ በርስያን ጋር ሁለተኛውን ሚስዮን ጀመረ (የሐዋ. ፲፭፡ ፴፪፣ ፴፣ ፴፭)።
8. ጠርሴስ የጳውሎስ ቤት ከተማ፣ ጳውሎስ በወንድሞች ህይ ወቱን ለመጠበቅ ወደ እዚህ ተልኮ ነበር (የሐዋ. ፱፡ ፳፱–፴)።
9. ቆጵሮስ ከተሰደደ በኋላ፣ አንዳንድ ቅዱሳን ከእዚህ ምድር ሸሹ (የሐዋ. ፲፩፡ ፲፱)። ጳውሎስ በመጀመሪያው የሚስዮን ጉዞው በቆጵሮስ በኩል ተጓዘ (የሐዋ. ፲፣፡ ፭–፭)፣ በኋላም በርናባስና ማርቆስ በእዚህ ተጓዙ (የሐዋ. ፲፭፡ ፴፱)።
10. ጴፉ ጳውሎስ በእዚህ ቦታ አስማተኛን ረገመ (የሐዋ. ፲፣፡ ፮–፲፩)።
11. ደርቤ ጳውሎስ እና በርናባስ በዚህ ከተማ ወንጌልን ሰበኩ (የሐዋ. ፲፬፡ ፮–፯፣ ፳–፳፩)።
12. ልስጥራ ጳውሎስ አካለ ስንኩልን ሲፈውስ፣ እርሱ እና በር ናባስ እንደ አምላኮች ሰላምታ ተሰጣቸው። ጳውሎስ ተናገረ እናም የሞተ መሰላቸው ነገር ግን ተነሳ እናም መስበክን ቀጠለ (የሐዋ. ፲፬፡ ፮–፳፩)። የጢሞቴዎስ ቤት (የሐዋ. ፲፮፡ ፩–፣)።
13. ኢቆንዮን በመጀመሪያው ሚስዮናቸው፣ ጳውሎስ እና በር ናባስ በእዚህ ቦታ ሰበኩ እናም ለመወገር አስፈራርተዋቸው ነበር (የሐዋ. ፣፣፡ ፶፭–፲፡ ፯)።
14. ሎዶቅያ እና ቈላስይስ ሎዶቅያ ጳውሎስ ከጎበኛቸው እና ደብዳቤ ከተቀበለባቸው የቤተክርስቲያኗ ቅርንጫፎች አንዱ ነው (ቈላ. ፬፡ ፲፮)። በዮሐንስ ራዕይ ውስጥ ከተጠቀሱት ሰባት ከተማዎች አንዱም ነው (ሌሎቹም ኤፌሶን፣ ስምርኔስ፣ ጴርጋሞን፣ ትያጥሮን፣ ሰርዴስ፣ እና ፊልድልፍያ ናቸው፣ ራዕ. ፩፡ ፲፩ ተመልከቱ)። ቈላስይስ ከሎዶቅያ በ ፲፯ ኪሎ ሜትር ወደ ምስራቅ ይገኛል። ጳውሎስ በእዚህ ለሚኖሩት ቅዱሳን ጻፈ።
15. አንጾኪያ (በጲስድያ ውስጥ) በመጀመሪያው ሚስዮናቸው፣ ጳውሎስና በርናባስ አይሁዶችን ክርስቶስ ከዳዊት ዘር እንደ መጣ አስተማሩ። ጳውሎስ ወንጌሉን ለእስራኤል አቀረበ፣ ከእዚያም ለአህዛብ አቀረበ። ጳውሎስ እና በርናባስ ተሰደዱ (የሐዋ. ፣፣፡ ፲፡–፱)።
16. ሚሊጢን በሶስተኛው ሚስዮኑ ላይ እያለ፣ ጳውሎስ የቤተክ ርስቲያኗን ካህናት “ጨካኞች ተኩላዎች” በመንጋዎች መካ ከል እንደሚገቡ አስጠናቀቀ (የሐዋ. ፳፡ ፳፱–፴፩)።
17. ፍጥሞ በዮሐንስ ራዕይ ውስጥ የነበሩትን ራዕዮች በተቀበለበት ጊዜ ዮሐንስ በእዚህ ደሴት ላይ እስረኛ ነበር (ራዕ. ፩፡ ፱)።
18. ኤፌሶን አጵሎስ በእዚህ ቦታ በሀይል ሰበከ (የሐዋ. ፲፰፡ ፳፬–፳፰)። ጳውሎስ፣ በሶስተኛው ሚስዮን፣ በኤፌሶን ውስጥ ለሁ ለት አመት አስተማረ፣ ብዙ ሰዎችን ቀየረ (የሐዋ. ፲፱፡ ፣፡ ፲፡)። በእዚህም መንፈስ ቅዱስ ስጦታን እጆችን በመጫን ሰጠ (የሐዋ. ፲፱፡ ፩–፯)፣ እናም ክፉ መንፈሶችን ከማስወጣት በተጨ ማሪ ብዙ ታዕምራቶችን ሰራ (የሐዋ. ፲፱፡ ፡፡–፳፩)። አርጢምስ በጳውሎስ ላይ ብጥብጥ አመጣ (የሐዋ. ፲፱፡ ፳፪–፴፩)። የዮሐ ንስ ራዕይ መፅሐፍ ክፍልም በኤፌሶን ስላለው ቤተክርስቲያን ነው (ራዕ. ፩፡ ፲፩)።
19. ጢሮአዳ ጳውሎስ በእዚህ ቦታ በሁለተኛው ሚስዮን በሚ ጓዙበት ጊዜ፣ እርዳታ የሚጠይቅ ሰው በመቄዶንያ ውስጥ በራዕይ አየ (የሐዋ. ፲፮፡ ፱–፲፪)። ለሶስተኛው ሚስዮን በእ ዚህ ቦታ እያለ፣ ጳውሎስ አውጢኪስን ከሞት አስነሳ (የሐዋ. ፳፡ ፯–፲፪)።
20. ፊልጵስ ጳውሎስ፣ ሲላስ፣ እና ጢሞቴዎስ ሉድ የምት ባል ሴትን ቀየሩ፣ ክፉ መንፈስን አስወጡ፣ እናም ተደበ ደቡ (የሐዋ. ፲፮፡ ፲፩–፳፫)። ከእስር ቤት ለማምለጥ መለኮ ታዊ እርዳታ ተቀበሉ (የሐዋ. ፲፮፡ ፳፫–፳፮)።
21. አቴና ጳውሎስ፣ ወደ አቴና በሄደው በሁለተኛው ሚስዮኑ፣ በማርስ ኮረብታ (አርዮስፋጎስ) ላይ “ስለማይታወቅ አምላክ” ሰበከ (የሐዋ. ፲፯፡ ፳፪–፴፩)።
22. ቆሮንቶስ ጳውሎስ ለሁለተኛ ሚስዮኑ ወደ ቆሮንቶስ ሄደ፣ በእ ዚህም ከአቂላ ና ከጵርስቅላ ጋር ኖረ። በእዚህም ሰበከ እናም ብዙ ሰዎችን አጠመቀ (የሐዋ. ፲፰፡ ፩–፲፰)። ከቆሮንቶስ፣ ጳውሎስ ወደ ሮሜ መልእክትን ጻፈ።
23. ተሰሎንቄ ጳውሎስ በሁለተኛው የሚስዮን ጉዞው በእዚህ ቦታ ሰበከ። የሚስዮን ቡድኑ አይሁዶች ደህንነታቸውን ካስፈራራ ቸው በኋላ ወደ ቤርያ ሄዱ (የሐዋ. ፲፯፡ ፩–፣)።
24. ቤርያ ጳውሎስ፣ ሲላስ፣ እና ጢሞቴዎስ በጳውሎስ ሁለተኛ ጉዞ የሚያስተምሯቸው ልውል ነፍሶችን አገኙ (የሐዋ. ፲፯፡ ፣–፲፣)።
25. መቄዶንያ ጳውሎስ በሁለተኛው እና በሶስተኛው ጉዞው በእ ዚህ ቦታ አስተማረ (የሐዋ. ፲፮፡ ፱–፴፣ ፲፱፡ ፳፭)። ጳውሎስ ለእርሱ እና በኢየሩሳሌም ላሉት ደሀ ቅዱሳን ለሰጡት ለመ ቄዶንያ ቅዱሳንን ደግነታቸውን አመሰገናቸው (ሮሜ ፲፭፡ ፳፮፣ ፪ ቆሮ. ፰፡ ፩–፭፣ ፲፩፡ ፱)።
26. መላጥያ ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሲሄድ በእዚህ ደሴት ላይ መርከቡ ተሰበረ (የሐዋ. ፳፯፡ ፴፪፣ ፳፰፡ ፩–፴)። በእባብ ቢነከ ሰም አልተጎዳም እናም በመላጥያ የታመሙትን ሁሉ ፈወሰ (የሐዋ. ፳፰፡ ፩–፱)።
27. ሮሜ ጳውሎስ በቤት ውስጥ ታስሮ እያለ ለሁለት አመት በእዚህ ቦታ ሰበከ (የሐዋ. ፳፰፡ ፲፯–፴፩)። በሮሜ ውስጥ ታስሮ እያለ መልእክቶች፣ ወይም ደብዳቤዎች፣ ለኤፌሶን፣ ለፊልጵስዩስ፣ እና ቈላስይስ እናም ለጢሞቴዎስና ለፊልሞና ጻፈ። ጴጥሮስ የመጀመሪያ መልእክቱን ኔሮ ክርስቲያኖችን በ፷፬ ዓ.ም. ካሳ ደደ በኋላ ምናልባት ሮሜ ከሆነው “ከባቢሎን” ጻፈ። ጴጥሮስ እና ጳውሎስ በእዚህ ቦታ ሰማዕት እንደሆኑ ይታመናል።

14. የቅዱስ ምድር ከፍታ



የመፅሐፍ ቅዱስ ካርታዎች ዝርዝር

የካርታዎች ዝርዝር በካርታዎች ላይ አንድ ቦታን ለማግኘት ይረዳችኋል። እያንዳንዱ ቦታ የካርታ ቁጥር እና መጠቆሚያ በቁጥር እና በፊደል የተሰራ ነው። ለምሳሌ ረባት (አማን) 1:መ5 ተሰጥቷል፣ ይህም ካርታ 1፣ አራት መአዘን መ5 ማለት ነው። የቦታዎቹ ሌላ ስም በቅንፎች ውስጥ ተዘርዝረዋል፣ ለምሳሌ፣ ረባት (አማን)። ከስም በኋላ የሚገኝ የጥ ያቄ ምልክት በካርታው ላይ የሚታየው ቦታ ትክክል እንደሆነ የሚገመትበት እንጂ እርግጠኛ እንዳልሆነ ያመለክታል።

ሀስሞኔአን ቤተ መንግስት፣ በኢየሩሳሌም ውስጥ, 12:ሐ5
ሁለቱ ወንዞች መካከል (ሐራን), 9:ሠ2
[የ]ሁሌኽ ሀይቅ (የማሮን ውኃ), 10:ሐ2, 14:ሐ6
[የ]ሁሌኽ ሸለቆ, 1:ሐ2, 11:ሐ2
[የ]ሂስፓኛ ክልል, 8:ሀ2
ሄሊኦፖሊስ (ኦን), 2:ሀ3
[የ]ሄሮድስ ቤተመንግስት፣ በኢየሩሳሌም ውስጥ, 12:ለ5
ሄኖም ሸለቆ፣ በኢየሩሳሌም ውስጥ, 12:ለ7

[የ]ሕዝቅያስ ዋሻ፣ በኢየሩሳሌም ውስጥ, 12:ሐ6
[የ]ሖር ሰዎች, 9:ሠ2
[የ]ሖር ተራራ, 2:መ2

ለኪሶ, 1:ለ6, 3:ለ6, 4:ለ4, 10:ለ7
[የ]ሉቅያ ክልል, 13:ረ2
[የ]ሉድ ክልል, 13:ሠ2
ሊቢያ, 8:ለ3, 13:ሐ4
[የ]ሊቢያ በረሀ, 9:ለ4
ሊባኖስ ተራራ, 1:ሐ1, 10:ሐ1, 11:ሐ1
[የ]ሊታኒ ወንዝ, 1:ሐ1, 10:ሐ1, 11:ሐ2
ሌሳ (ዳን), 10:ሐ2
ልስጥራ, 13:ሰ2
ሎዛ (ቤቴል), 10:ለ5
ሎዶቅያ, 13:ረ2

ሐሴቦን, 4:ሐ4
ሐራን (ሁለቱ ወንዞች መካከል), 9:ሠ2

መሃናይም, 10:ሐ5
መላጥያ (ማልታ), 13:ለ3
መልካም ወደብ, 13:ሠ3
መልካም ደጅ, 12:ሐ4
መስጴጦምያ, 8:መ3, 9:ሠ2
[የ]መቄዶንያ ክልል, 7:ሀ2, 8:ሐ2, 13:መ1
[የ]መቅደስ ደረጃዎች፣ በኢየሩሳሌም ውስጥ, 12:መ5
መጊዶ, 1:ለ3, 3:ለ3, 4:ለ2, 6:ለ3, 9:መ3, 10:ለ3
መጌዶል, 11:ሐ3
ሙራ, 13:ረ2
[ወደ] ሙት ባህር የሚመራ መንገድ, 12:ሐ8
[የ]ሙት ባህር (የጨው ባሕር), 1:ሐ7, 2:መ1, 3:ሐ6, 4:ሐ4, 9:መ4, 10:ሐ6, 11:ሐ7, 14:ሀ7, 14:ሐ3
[የ]ሙት ባህር ዝቅተኛ ቦታ, 14:ሐ3
[የ]ሙት ባህር ዝቅታና ከፍታ, 14:ሀ7, 14:ሐ3
ሚሊጢን, 13:ሠ2
[የ]ሚስያ ክልል, 13:ሠ1
[የ]ማልታ ደሴት, 13:ለ3
ማራ, 2:ለ3
[የ]ማሮን ውኃ (የሁሌኽ ሀይቅ), 10:ሐ2
[የ]ሜድትሬኒያን (ታላቅ፣ ከፍተኛው) ባህር, 1:ሀ4, 2:ለ1, 3:ሀ3, 4:ሀ3, 5:ሀ3, 6:ሀ3, 7:ሀ3, 8:ለ3, 9:ለ3, 10:ሀ4, 11:ሀ5, 13:መ3, 14:ሀ2, 14:ሀ6
[የ]ሜድትሬኒያን ባህር ዝቅታና ከፍታ, 14:ሀ2, 14:ሀ6
ማኬሩስ, 11:ሐ7
ማይሲኔአ, 5:ሀ2
ሜምፎስ (ኖፍ), 2:ሀ3, 5:ለ4, 6:ለ3, 7:ሀ3, 8:ሐ3
ሜር ኢንተርኑም (ታላቅ ከፍተኛው የሜድትሬኒያን ባህር), 8:ለ3
ሜድባ, 4:ሐ4
ሜዶናዊ ግዛት, 6:መ3
[የ]ምስራቅ (የበታች) ባህር, 5:ሐ4, 6:ሐ4
[የ]ምስራቅ ምድረበዳ, 2:መ2
ምናሴ፣ ጎሳ, 3:ለ4, 3:መ2
[የ]ምድረበዳ ስፍራ, 2:ሐ4
[የ]ምድያም ክልል, 2:መ4, 9:ሠ4
[የ]ሞሪያ ተራራ, 14:ለ6
[የ]ሞሬ ኮረብታ, 1:ሐ3, 10:ሐ3
[የ]ሞአብ ሜዳ, 1:ሐ6, 11:ሐ6
[የ]ሞአብ ክልል, 1:መ7, 2:መ1, 3:መ7, 4:ሐ5, 10:መ7

ሦስት ማደሪያ, 13:ለ1

ረባት (አማን), 1:መ5, 3:መ5, 10:መ5, 14:መ2
[የ]ሩድ ደሴት, 9:ለ3, 13:ሠ3
ራምሴ (ታኒስ), 2:ለ2
ራፊዲም, 2:ሐ4
ራፋታ, 2:ሐ4
ሬጊዩም, 13:ለ2
[የ]ሮቤል ጎሳ, 3:ሐ6
ሮሜ, 8:ለ2, 13:ሀ1

[የ]ሰለሞን ሰቀላ፣ በኢየሩሳሌም ውስጥ, 12:መ4
[የ]ሰሌሆም መጠመቂያ ገንዳ፣ በኢየሩሳሌም ውስጥ, 12:ሐ7
ሰማርያ, 1:ለ4, 5:ለ3, 10:ለ4, 11:ለ5, 13:ሸ3
[ወደ] ሰማርያ የሚመራ መንገድ, 12:ለ1
[የ]ሰማርቲያ ክልል, 8:ሐ1
[የ]ሰማርያ ክልል, 1:ለ4, 10:ለ4, 11:ለ4
ሰምርኔስ, 13:ሠ2
ሰራኩስ, 13:ለ2
ሰራፕታ, 11:ለ1
ሰናዖር (ባቢሎን), 9:ሰ3
[የ]ሰዶም እና የገሞራ አካባቢ, 10:ሐ8
ሰገነት፣ በኢየሩሳሌም ውስጥ, 12:ለ6
ሱሳ, 6:ሐ3, 7:ለ3, 9:ሰ3
[የ]ሱሳ በር፣ በኢየሩሳሌም ውስጥ, 12:መ4
[የ]ሱር ምድረበዳ, 2:ሐ2

ሱኮት፣ በእስራኤል ውስጥ, 3:ሐ4, 4:ሐ3
ሱኮት፣ በግብፅ ውስጥ, 2:ለ2
[የ]ሱዌዝ የባህር ሰሌጣ, 2:ለ4
[የ]ሲና ተራራ (ኮሬብ), 2:ሐ4, 9:መ4
[የ]ሲና ምድረበዳ, 2:ሐ4
[የ]ሲን ምድረበዳ, 2:ሐ3
ሲካር, 11:ለ5
ሲዶን, 1:ሐ1, 9:መ3, 10:ለ1, 11:ለ1, 13:ሸ3
ሳሌም, 11:ሐ4
ሳሌም (ኢየሩሳሌም), 9:መ3
ሳሞጥራስ ደሴት, 13:ሠ1
ሳቢላኒስ፣ ክልል, 11:መ1
ሴሎ, 3:ለ5, 4:ሐ3, 10:ሐ5
ሴኬም, 3:ለ4, 4:ሐ3, 10:ለ4
ስልማና, 13:ሰ3
[የ]ስምዖን ጎሳ, 3:ሀ7
[የ]ሶሬቅ ወንዝ, 1:ለ6, 10:ሀ6, 11:ሀ6
[የ]ሶርያ ክልል, 6:ለ3, 8:ሐ3, 9:መ3, 11:ሐ2, 13:ሸ3
ስፓርታ, 6:ሀ2, 7:ሀ2
[የ]ሼረን ሜዳ, 1:ለ4, 10:ለ4, 11:ለ5
ሼፌላህ, 1:ለ6, 10:ለ6, 14:ለ2

ቀሬና, 13:መ3
[የ]ቀሬና ክልል, 13:ሰ2
ቀርሜሎስ ተራራ, 1:ለ3, 3:ለ3, 4:ለ2, 10:ለ3, 11:ለ3
ቀርጤስ (ክፍቶር) ደሴት, 8:ሐ3, 9:ሀ3, 13:ሠ3
ቀኒዶስ, 13:ሠ2
ቀይ ባሕር, 2:መ4, 5:ለ4, 6:ለ4, 7:ለ4, 8:ሐ4, 9:መ4
[የ]ቀያፋ ቤት፣ በኢየሩሳሌም ውስጥ, 12:ለ6
[የ]ቀጰዶቅያ ክልል, 13:ሸ2
ቂሣርያ, 11:ለ4, 13:ሸ3
ቂርሐራሴት, 10:ሐ7
[የ]ቂሶን ወንዝ, 1:ለ3, 10:ለ3, 11:ለ3
ቃና, 11:ሐ3
ቃዴስ በርኔ, 2:ሐ2, 3:ሀ8, 4:ሀ6
ቄድሮን ሸለቆ፣ በኢየሩሳሌም ውስጥ, 12:መ6
ቅፍርናሆም, 11:ሐ3
ቆሮንቶስ, 13:መ2
ቆጵሮስ (ኪቲም) ደሴት, 8:ሐ3, 9:ሐ3, 13:ሰ3

በሬማት ዘገለዓድ, 3:መ3, 4:ሐ2
[የ]በሳን ክልል, 1:መ2, 10:ሐ2
በውሀ የተከበበ ሲና, 2:ሐ3
በግ በር፣ በኢየሩሳሌም ውስጥ, 12:ሐ4
ቢታንያ, 11:ለ6
[ወደ] ቢታንያ የሚመራ መንገድ, 12:መ6
[የ]ቢታንያ ክልል, 13:ረ1
[የ]ቢንያም ጎሳ, 3:ሀ5
ባሶራ, 4:ሐ6
ባቢሎን, 5:ሐ3, 6:ሐ3, 7:ለ3, 9:ረ3
ባቢሎን (ሰናዖር), 9:ሰ3
[የ]ባቢሎን ክልል, 9:ረ3
[የ]ባቢሎን ግዛት፣ አዲስ, 6:ለ3
ቤርሳቤህ, 1:ለ7, 2:ሐ1, 3:ለ7, 4:ለ5, 9:መ4, 10:ለ7, 11:ሀ8
ቤርያ, 13:መ1
ቤተ ልሔም, 1:ለ6, 3:ለ6, 4:ለ4, 10:ለ6, 11:ለ6
[ወደ] ቤተ ልሔም የሚመራ መንገድ, 12:ሀ7
[የ]ቤተመቅደስ ጫፍ፣ በኢየሩሳሌም ውስጥ, 12:መ5
ቤተ ሳይዳ, 11:ሐ3
[የ]ቤተ ሳይዳ የረጋ ውሀ ፈሳሽ፣ በኢየሩሳሌም ውስጥ, 12:ሐ3
ቤተ ራባ, 11:ሐ6
ቤተ ፋጌ, 11:ለ6
ቤተመቅደስ፣ በኢየሩሳሌም ውስጥ, 12:ሐ4
ቤቴል (ሎዛ), 3:ለ5, 4:ሐ4, 10:ለ5, 11:ለ6
ቤትሳን, 3:ሐ3, 4:ሐ3, 10:ሐ4
ቤዜጣ, 12:ለ3
ብሪታንያ ክልል, 8:ሀ1
[የ]ቦሦር ወንዝ, 1:ሀ7, 10:ሀ7, 11:ሀ8

ተሰሎንቄ, 8:ሐ2, 13:መ1
ታላቅ (የከፍተኛው ሜድትሬኒያን) ባህር, 1:ሀ4, 2:ለ1, 3:ሀ3, 4:ሀ3, 5:ሀ3, 6:ሀ3, 9:ለ3, 10:ሀ4, 11:ሀ5, 14:ሀ2, 14:ሀ6
[የ]ታቦር ተራራ, 1:ሐ3, 3:ሐ3, 4:ሐ2, 10:ሐ3, 11:ሐ3, 14:ሐ6
[የ]ታችኛው ባህር (የምስራቅ ባህር፣ ፋርሳዊው ባህር ሰሌጣ), 5:ሐ4, 6:ሐ4, 7:ለ4, 8:መ4, 9:ሸ3
ታኒስ (ራምሴ), 2:ለ2
[የ]ታይግረስ ወንዝ, 5:ሐ2, 6:ሐ2, 8:መ3, 9:ሰ3
ቴቁሔ, 10:ለ6
ቴቢስ, 5:ለ4, 6:ለ4, 7:ሀ4, 8:ሐ4
ትሮይ, 9:ለ2, 6:ሀ2, 7:ሀ2

ነነዌ, 5:ሐ2, 9:ረ2
[የ]ናባ ተራራ, 1:ሐ6, 2:መ1, 3:ሐ6, 4:ሐ4, 10:ሐ6, 11:ሐ6
[የ]ናባቴአ ክልል, 11:ሐ8
ናዝሬት, 1:ሐ3, 11:ለ3
ናይን, 11:ሐ4
[የ]ናይል ወንዝ, 2:ሀ4, 5:ለ4, 6:ለ4, 7:ሀ4, 8:ሐ4, 9:ሐ4
[የ]ናይል ደለል, 2:ሀ2, 9:ሐ4
[የ]ኔጌቭ ክልል, 1:ለ8, 10:ለ8
ንጉሳዊ በረንዳ፣ በኢየሩሳሌም ውስጥ, 12:ሐ5
[የ]ንፍታሌም ጎሳ, 3:ሐ2

አማሌቅ፣ ክልል, 4:ሀ6
አማን (ራባት), 1:መ5, 10:መ5, 14:መ2
አሞን፣ ክልል, 1:መ6, 3:መ5, 4:መ3, 10:መ6
አስቀሎና (አስከሎና), 1:ሀ6, 3:ሀ6, 4:ሀ4, 10:ሀ6, 11:ሀ6
አስከሎን (አስቀሎና), 11:ሀ6
[የ]አሮዖን ወንዝ, 1:ሐ7, 2:መ1, 3:ሐ6, 4:ሐ5, 10:ሐ7, 11:ሐ7
አሦር, 5:ሐ2, 9:ረ2
[የ]አሴር ጎሳ, 3:ለ2
[የ]አስሩ ከተማ ክልል, 11:መ4
አሶር, 9:ረ2
[የ]አሶር ግዛት, 5:ሐ3

አዞር (በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሶር ነው), 3:ሐ2, 4:ሐ2, 10:ሐ2
አረብ, 5:ሐ4, 8:መ4
[የ]አረባውያን በረሀ, 9:ረ3
[የ]አረባውያን ባህር, 6:መ4
አሪማቴያ, 11:ለ5
አራል ባህር, 5:መ1, 6:መ1, 7:ሐ2
አራም-ደማስቆ፣ ክልል, 4:መ1
አራራት ተራራ, 9:ረ1
አርሞንዔም, 1:መ1, 3:ሐ1, 4:ሐ1, 10:ሐ1, 11:ሐ1, 14:መ5
አርካድ (አካድ)፣ ክልል, 9:ሰ2
አርንብ፣ ክልል, 4:ሐ1
አቃሮን, 1:ለ6, 10:ሀ6
[የ]አቃባ ባህረ ሰሌጣ, 2:መ4
አባና፣ ወንዝ, 1:መ1
አቴና, 6:ሀ2, 7:ሀ2, 8:ሐ2, 13:መ2
[የ]አትክልት ስፍራ መቃብር፣ በኢየሩሳሌም ውስጥ, 12:ለ3
[የ]አንቶኒያ ትልቅ ምሽግ፣ በኢየሩሳሌም ውስጥ, 12:ሐ3
አንጾኪያ፣ በአሶር ውስጥ, 8:ሐ3, 13:ሸ2
አንጾኪያ፣ በጲስድያ ውስጥ, 13:ረ2
አካይያ፣ የሮሜ ክልል, 8:ሐ2, 13:መ2
አካድ (አርካድ)፣ ክልል, 9:ሰ2
አወኩ, 13:ሰ2
አዛጦን, 1:ሀ6, 3:ሀ5, 4:ለ4, 10:ሀ6, 11:ሀ6
[የ]አድርያ ባህር (አድሪያትክ), 8:ለ2
አፍዩስ ፋሩስ, 13:ለ1
[የ]ኡራርቱ ክልል, 9:ሠ1
[የ]ኢንዱስ ወንዝ, 7:መ3
ኢየሩሳሌም (ሳሌም), 1:ለ6, 2:መ1, 3:ለ5, 4:ሐ4, 5:ለ3, 6:ለ3, 7:ሀ3, 8:ሐ3, 9:መ3, 10:ለ6, 11:ለ6, 13:ሸ3, 14:ለ2, 14:ለ6
ኢየሩሳሌም፣ የከተማዋ ታችኛ ቦታ, 12:ሐ6
ኢየሩሳሌም፣ የከተማዋ ከፍተኛ ቦታ, 12:ለ6
ኢያሪኮ, 1:ሐ5, 2:መ1, 3:ሐ5, 4:ሐ4, 10:ሐ6, 11:ሐ6, 14:ሀ7, 14:ሐ3
[ወደ] ኢያሪኮ የሚመራ መንገድ, 12:መ6
ኢያቢስ ገለዓድ, 3:ሐ4
ኢይዝራኤል, 4:ሐ2, 10:ለ4
[የ]ኢይዝራኤል (እስድሬሎን) ሸለቆ, 1:ለ3, 10:ለ3
ኢዮጴ, 1:ሀ5, 3:ሀ5, 4:ለ3, 10:ሀ5, 11:ሀ5, 13:ሸ3
[ወደ] ኢዮጴ የሚመራ መንገድ, 12:ሀ4
[የ]ኢዱሜአ ክልል, 1:ለ8, 10:ለ8, 11:ለ7
ኢጣልያ፣ የሮሜ ግዛት, 8:ለ2, 13:ሀ1
ኤሊም, 2:ሐ3
ኤላ, 1:ለ6, 10:ሀ6, 11:ሀ6
[የ]ኤላም ክልል, 5:ሐ3, 6:ሐ3, 7:ሐ3, 9:ሸ3
[የ]ኤማሁስ መንገድ, 12:ሀ4
ኤሎን, 1:ለ5, 10:ለ5, 11:ለ5
ኤማሁስ, 11:ለ6
[የ]ኤታም ምድረበዳ, 2:ለ3
ኤኢኖን, 11:ሐ4
[የ]ኤዊያውያን ህዝብ, 3:ሐ1
[የ]ኤዶም ክልል, 1:ሐ8, 2:መ2, 4:ሐ7, 10:መ8
ኤፌሶን, 8:ሐ2, 13:ሠ2
[የ]ኤፍራጥስ ወንዝ, 5:ለ3, 6:ለ3, 8:መ3, 9:ሠ2
[የ]ኤፍሬም ጎሳ, 3:ለ5
[የ]እስራኤል መጠመቂያ ገንዳ፣ በኢየሩሳሌም ውስጥ, 12:ሐ4
[የ]እስራኤል ክልል, 4:ለ3
እስክንድርያ, 8:ሐ3, 13:ረ4
[የ]እስያ የሮሜ ግዛት, 8:ሐ2, 13:ረ1
[የ]እስድሬሎን (ኢይዝራኤል) ሸለቆ, 1:ለ3, 10:ለ3
[የ]እባብ መጠመቂያ ገንዳ፣ በኢየሩሳሌም ውስጥ, 12:ሀ6
ኦን (ሄሊኦፖሊስ), 2:ሀ3, 9:ሐ4

ከርከሚሽ, 5:ለ2, 6:ለ2, 9:መ2
[የ]ከነዓን ክልል, 2:ሐ1, 9:መ3
ከፍተኛው (ታላቅ የሜድትሬኒያን) ባህር, 7:ሀ3, 9:ለ3
[የ]ከፍቶር (ቀርጤስ) ደሴት, 9:ሀ3
[የ]ኪኔሬት ባህር (ገሊላ), 1:ሐ3, 3:ሐ2, 4:ሐ2, 9:መ3, 10:ሐ3, 11:ሐ3
ኪቲም (ቆጵሮስ) ደሴት, 9:ሐ3
ኪዩ, 13:ሠ2
ካርተጅ, 8:ለ3
[የ]ካስፒየን ባህር, 5:ሐ1, 6:ሐ2, 7:ለ2, 8:መ2, 9:ሰ1
ኬብሮን, 1:ለ6, 2:መ1, 3:ለ6, 4:ለ4, 10:ለ7, 11:ለ7
[የ]ኬጢያውያን ህዝብ, 9:መ2
ኮራዚ, 11:ሐ3
ኮሬብ (ሲና ተራራ), 2:ሐ4, 9:መ4
[ወደ] ኬብሮን የሚመራ መንገድ, 12:ሀ7
[የ]ኮከሱሥ ተራራ, 5:ሐ1, 8:መ2, 9:ረ1

[የ]ውኃው በር፣ በኢየሩሳሌም ውስጥ, 12:ሐ7

ዑር, 5:ሐ3, 9:ሠ2, 9:ሰ3
ዓሳ በር፣ በኢየሩሳሌም ውስጥ, 12:ለ3
ዓረባ (የተሰነጠቀ ሸለቆ), 1:ሐ8, 2:መ2, 4:ሐ6, 10:ሐ8
ዓራድ, 2:መ1, 3:ለ7, 4:ለ5
[የ]ዔባል ተራራ, 1:ለ4, 3:ለ4, 4:ሐ3, 10:ለ4, 11:ለ5, 14:ለ6
ዓኮን (አኮ፣ ፕቶሌሚያስ), 1:ለ3, 3:ለ2, 4:ለ2, 10:ለ2, 11:ለ3
ዓይንሮጌል ምንጭ, 12:ሐ7
ዓይንዶር, 10:ሐ3
ዓይንጋዲ, 4:ሐ4, 10:ሐ7
ዔጽዮንጋብር, 2:መ3, 4:ለ8, 9:መ4

[የ]ዘሬድ ወንዝ, 1:ሐ8, 2:መ2, 3:ሐ8, 4:ሐ5, 10:ሐ8, 11:ሐ8
[የ]ዛብሎን ጎሳ, 3:ለ3

[ከ]ዮርዳኖስ አልፎ ያለ የምስራቅ ከፍ ያለ ጠፍጣፋ ቦታ, 14:መ2
[የ]ዮርዳኖስ ወንዝ, 1:ሐ5, 2:መ1, 3:ሐ5, 4:ሐ3, 10:ሐ5, 11:ሐ5
[የ]ያርሙክ ወንዝ, 1:ሐ3, 10:ሐ3, 11:ሐ3
[የ]ያቦቅ ወንዝ, 1:ሐ5, 3:መ4, 4:መ3, 10:ሐ5, 11:ሐ5

[የ]ይሁዳ ምድረበዳ, 1:ለ7, 11:ለ7
ይሁዳ፣ ክልል, 1:ለ6, 11:ለ7
[የ]ይሁዳ ክልል, 5:ለ3, 10:ለ7
[የ]ይሁዳ የኩረብታ አገር, 14:ለ2
ይሁዳ፣ ጎሳ, 3:ሀ6
[የ]ይሳኮር ጎሳ, 3:ሐ3
ደማስቆ, 1:መ1, 9:መ3, 10:መ1, 11:መ1, 13:ሸ3
ደርቤ, 13:ሰ2
ደብረ ዘይት ተራራ, 1:ለ6, 10:ለ6, 11:ለ6, 12:መ5, 14:ለ6
ዱራ, 9:ረ3
[የ]ዳቺያ ክልል, 8:ሐ2
ዳን (ሌሳ), 1:ሐ2, 3:ሐ1, 4:ሐ1, 10:ሐ2
ዳን፣ ጎሳ, 3:ሐ1, 3:ሀ5
ዴቦን, 2:መ1
ዶር, 3:ለ3, 4:ለ2
ዶታይን, 10:ለ4
[የ]ጀርማኒያ ክልል, 8:ለ1

[የ]ገለዓድ ክልል, 1:ሐ4, 10:ሐ4
[የ]ገሊላ ባህር (ኪኔሬት), 1:ሐ3, 3:ለ2, 4:ሐ2, 9:መ3, 10:ሐ3, 11:ሐ3, 14:ለ7
[የ]ገሊላ ከፍተኛ ክልል, 1:ሐ2
[የ]ገሊላ ክልል, 11:ሐ3
ገሊላ የበታች ክልል, 1:ሐ3
[የ]ገላትያ ክልል, 13:ሰ1
[የ]ገሞራ እና የሰዶም አካባቢ, 10:ሐ8
ገሪዛን ተራራ, 1:ለ5, 3:ለ4, 4:ሐ3, 10:ለ5, 11:ለ5, 14:ለ6
ገባዖን, 10:ለ5
[የ]ጊልቦዓ ተራራ, 1:ሐ4, 3:ሐ3, 10:ሐ4, 11:ሐ4, 14:ሐ6
ጊብዓ, 4:ሐ4
ጋትሔፌር, 10:ለ3
[የ]ጋኡል ክልል, 8:ሀ1
ጋዛ, 1:ሀ6, 2:ሐ1, 3:ሀ6, 4:ሀ4, 10:ሀ7, 11:ሀ7, 13:ሸ4
ጋይ, 2:መ1, 10:ለ5
[የ]ጋድ ጎሳ, 3:ሐ5
[የ]ጌራራ ወንዝ, 1:ሀ7, 10:ሀ7, 11:ሀ7
[የ]ጌሜም ክልል, 2:ሀ2, 9:ሐ4
[የ]ጌሹር ክልል, 4:ሐ3
ጋዳራ, 11:ሐ4
ጌልገላ, 1:ሐ5, 2:መ1, 4:ሐ4
ጌራራ, 10:ሀ7
ጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ፣ በኢየሩሳሌም ውስጥ, 12:መ4
ጌት, 3:ሀ6, 4:ለ4, 10:ሀ6
ጌዝር, 4:ለ4
[የ]ግብፅ መንግስት, 6:ሀ3
[የ]ግብፅ ክልል, 2:ሀ2, 5:ለ4, 7:ሀ4, 8:ሐ4, 9:ሐ4, 13:ረ4
[የ]ግብፅ ወንዝ, 2:ሐ2
[የ]ግንብ መጠመቂያ ገንዳ፣ በኢየሩሳሌም ውስጥ, 12:ለ5
ግሪክ, 7:ሀ2
[የ]ግዮን ምንጭ፣ በኢየሩሳሌም ውስጥ, 12:መ6
ጎልጎታ፣ በኢየሩሳሌም ውስጥ, 12:ለ3

ጠርሴስ, 13:ሰ2
ጢሮስ, 1:ለ2, 3:ለ1, 4:ለ1, 9:መ3, 10:ለ1, 11:ለ2, 13:ሸ3
ጢሮአዳ, 13:ሠ2
[የ]ጥቁር ባህር, 5:ለ1, 6:ለ1, 7:ለ2, 8:ሐ2, 9:ሐ1, 13:ረ1
ጥብርያዶስ, 11:ሐ3
[የ]ጨው ባሕር (የሙት ባህር), 1:ሐ7, 2:መ1, 3:ሐ6, 4:ሐ4, 9:መ4
[የ]ጲስድያ ክልል, 13:ረ2
[የ]ጳርጢአን ግዛት, 8:መ3
[የ]ጳንጦስ ክልል, 13:ሰ1
ጳፋ, 13:ሰ3
ጴሬአ, 11:ሐ5
ጴርጌ, 13:ረ2
ጴርጌሙም, 13:ሠ2
[የ]ጵንፍልያም ክልል, 13:ረ2

[የ]ጺን ምድረበዳ, 2:ሐ2
ጺቅላግ, 4:ሐ5

ፅዮን, 14:ለ6

ፊሀሒሮት, 2:ለ3
ፊልድልፍያ, 11:መ6
ፊልጵስዩስ, 13:መ1
ፊልጶስ ቂሣርያ, 11:ሐ2
ፊቶም, 2:ለ2
[የ]ፋራን ምድረበዳ, 2:ሐ3
ፋርሳዊው የባህር ሰሌጣ (የበታችኛው ባህር), 9:ሸ3
ፋርስ, 5:መ4, 6:መ4
[የ]ፋርፋ ወንዝ, 1:መ1, 10:መ1, 11:መ2
[የ]ፍልስጥኤም ህዝብ, 2:ሐ2
[የ]ፍልስጥኤም ሜዳ, 1:ሀ6, 10:ሀ6
[የ]ፍልስጥኤም ክልል, 4:ለ4
[የ]ፍርግያም ክልል, 13:ረ2
[የ]ፍጥሞ ደሴት, 13:ሠ2
[የ]ፎኒሲያ ክልል, 1:ሐ1, 4:መ1, 9:መ3, 10:ለ1, 11:ለ2, 13:ሸ3

ፕቲዮሎስ, 13:ለ1
ፓኒኤል, 10:ሐ4
ፕቶሌሚያስ (አኮ፣ ዓኮን), 1:ለ3, 11:ለ3, 13:ሸ3

የመፅሐፍ ቅዱስ ፎቶዎች

እነዚህ የአስፈላጊ ቦታዎች ፎቶዎች ኢየሱስ የተራመደበትን፣ የመፅሐፍ ቅዱስ ነቢያት የኖሩበትና ያስተማሩበትን፣ እና ብዙ የቅዱሳት መጻህፍት ድርጊቶች የተከናወኑበትን ቦታዎች ምሳሌ ያሳያሉ።

ማጠቃለያ

ከዚህ በታች የሚገኘው ካርታ በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉ ፎቶዎችን ቦታ የሚያሳይ ነው። በሚቀጥሉት ገጾች፣ እያንዳንዱ በቁጥር የሚለይ ፎቶ ስለሁኔታው የሚገልጹበት አለው። በዚያ አካባቢ የነበሩ ታላቅ ትርጉም ያላቸው የቅዱሳት መጻህፍት ድርጊቶች፣ ስለእነዚህ በተጨማሪ ለማንበብ የት ለመሄድ እንድታውቁም ከሚጠቁሙ የቅዱሳት መጻህፍት ጥቅሶቶች ጋር ተዘርዝረዋል።

1. አባይ ወንዝ እና ግብፅ
2. የሲና ተራራ (ኮሬብ) እና የሲና ምድረበዳ
3. የይሁዳ ምድረበዳ
4. ቃዴስ በርኔ
5. የአባቶች አለቃ መቃብር
6. የይሁዳ ተራራማው አገር
7. ቤተ ልሔም
8. ኢየሩሳሌም
9. የሄሮድስ ቤተመቅደስ
10. የቤተመቅደስ ደረጃዎች
11. ደብረ ዘይት ተራራ
12. ጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ
13. ጎልጎታ
14. የአትክልት ስፍራ መቃብር
15. ኢያሪኮ
16. ሴሎ
17. ሴኬም
18. ዶታይን በሰማርያ ውስጥ
19. ቂሣርያ እና ከሼረን እስከ ቀርሜሎስ ያለው ሜዳ
20. ኢዮጴ
21. ኢይዝራኤል ሸለቆ
22. ታቦር ተራራ
23. የገሊላ ባህር እና የታላቅ ደስታ ተራራ
24. ቅፍርናሆም
25. የዮርዳኖስ ወንዝ
26. ፊልጵስ ቂሣርያ
27. ናዝሬት
28. ዳን
29. አቴና
30. ቆሮንቶስ
31. ኤፌሶን
32. የፍጥሞ ደሴት



1. አባይ ወንዝ እና ግብፅ



በአባይ ወንዝ ዳር ያደጉት አትክልቶች። በእንደዚህ አይነት ቦታ፣ የሙሴ እናት ህጻን ወንድ ልጇን ደበቀች። የግብፅ አብዛኛውን ቦታ የሸፈነው በረሀ ከአትክልቶቹ በኋላ ይታያሉ።

ታላቅ ድርጊቶች፥ ምድሩ በግብፅዎስ ተገኝቶ ነበር (አብር. ፩፡፳፫–፳፭)። አብርሐም ወደ ግብፅ ሄደ (ዘፍጥ. ፲፪፡፲–፳፡ አብር. ፪፡፳፩–፳፭)። ጆሴፍ ወደ ግብፅ ተሸጠ፣ መሪ ሆነ፣ እናም ቤተሰቡን ከረሀብ አዳነ (ዘፍጥ. ፴፯፤ ፴፱–፴፯)። የያዕቆብ ትውልዶች በግብፅ ኖሩ (ዘፍጥ. ፴፯፤ ዘፀአ. ፩፣ ፲፪፡፴)። የፈርዖን ሴት ልጅ ህጻኑ ሙሴን በወንዙ ላይ አገኘችው እናም አሳደገችው (ዘፀአ. ፪፡፩–፲)። ሙሴ እስራኤላውያንን ከግብፅ መርቶ አወጣ (ዘፀአ. ፲–፲፬)። ማርያም፣ ዮሴፍ፣ እና ኢየሱስ ከሄሮድስ ለማምለጥ ለትንሽ ጊዜ ወደ ግብፅ ሄዱ (ማቴ. ፪፡፲፫–፲፭፣ ፲፱–፳፩)። በመጨረሻው ቀናት፣ ግብጻውያን ጌታን ያውቃሉ፣ እናም ጌታ ግብፅን ይባርካል (ኢሳ. ፲፱፡፳–፳፭)። (ቅ.መ.መ. ግብፅ ተመልከቱ።)

2. የሲና ተራራ (ኮሬብ) እና የሲና ምድረበዳ



ከእነዚህ ሁሉ የሚታወቁ ተራራዎች የሲና ተራራ ነው። አንዱ የባህል ቦታም፣ በዚህ ፎቶ የሚታየው ጀቤል ሙሳ (የሙሴ ተራራ) ነው።

ታላቅ ድርጊቶች፥ እግዚአብሔር በሙሴ ታየ እናም አስ ሩን ቃላት ሰጠው (ዘፀአ. ፲፱–፳)። ሙሴ፣ አሮን፣ ሁለቱ የአሮን ወንድ ልጆች፣ እና ፸ ሽማግሌዎች እግዚአብ ሔርን አዩ ግንኙነትም ነበራቸው (ዘፀአ. ፳፬፡ ፱–፲፪)። እግዚአብሔር ለሙሴ ታቦት የመገንቢያውን መመሪያ ሰጠው (ዘፀአ. ፳፭–፳፯፣ ፴–፴፩)። እስራኤላውያን አሮን እንዲሰራላቸው የገፋፉትን የወርቅ ጥጃ አመለኩ (ዘፀአ. ፴፪፡ ፩–፳)። ኤልያስ ንግስት ኤልዛቤል ከምትኖርበት ከኢይዝራኤል ሸለቆ ወደ እዚህ ምድር ሸሸ (፩ ነገሥ. ፲፱፡ ፩–፲፳)። ይህም ኤልያስ ከእግዚአብሔር ጋር የተነጋ ገረበት ቦታ ነው (፩ ነገሥ. ፲፱፡ ፳–፲፱)። (ቅ.መ.መ. የሲና ተራራ ተመልከቱ።)

3. የይሁዳ ምድረበዳ



የይሁዳ ምድረበዳ ከሙት ባህር እየወረደ በኢየሩሳሌም በስተምስራቅ በኩል ይገኛል።

ታሳቅ ድርጊቶች፣ የይሁዳ ምድረበዳ በመጀመሪያው ታሪክ ብዙ ዘመናት ውስጥ አስፈላጊ መሸሸጊያ ነበረ። ዳዊት ከንጉስ ሳዖል ተደበቀ (፩ ሳሙ. ፳፮፤ ፩–፫)። ኢየሱስ ለአርባ ቀን እና ለአርባ ሌሊት ጾመ (ማቴ. ፬፡ ፩–፲፩፤ ማር. ፩፡ ፲፪–፲፫)። ኢየሱስ በይሁዳ ምድረበዳ በኩል ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ ያለውን መንገድ የመልካሙ ሳምራዊ ምሳሌ ለመስጠት ተጠቀመበት፣ ምክንያቱም በዚህ አካባቢ ብቻቸውን የሚጓዙ በቀላል በአደጋ ላይ ስለሚወድቁ ነበር (ሉቃ. ፲፡ ፳፭–፴፯)። (ቅ.መ.መ. የሙት ባህር ተመልከቱ።)

4. ቃዴስ በርኔ



ይህ ቃዴስ በርኔ የሚገኝበት (ደግሞም ዋዲ ተብሎ የሚ ጠራው) የታላቁ የበረሀ ሸለቆ የሰሜን ምስራቅ እይታ ነው። በዝናብ ዘመን በዚህ የሚፈሰው ትንሽ ወንዝ ይህን በደንብ ውሀ የጠጣ እና የምድረበዳው ፍሬያማ ቦታ አድ ርጎታል።

ታላቅ ድርጊቶች፥ ይህ ሙሴ ፲፪ ሰዎች የከነዓን ምድ ርን እንዲሰልሉ የላከበት ቦታ ሳይሆን አይቀርም (ዘኁል. ፲፫፡፲፯–፴)። እስራኤላውያን በምድረበዳ በተንከራተቱ በት ፴ አመት ውስጥ ለ፴ አመት ይህ ቦታ እንደ ዋና ስፍ ራቸው ያገለግል ነበር (ዘዳግ. ፪፡፲፬)። ማርያም በዚህ ቦታ ውስጥ ሞታ ተቀበረች (ዘኁል. ፳፡፩)። የቆሬ አመጽ፣ የህዝቡ ማጉረምረም፣ እና የአሮን በትር እንቡጥ ማፍ ራት የነበሩት በዚህ ቦታ ነበር (ዘኁል. ፲፮–፲፯)። ከዚ ህም በሚቀርብ ቦታ ሙሴ ድንጋይን መታና ውሀ መጣ (ዘኁል. ፳፡፯–፲፩)።

5. የአባቶች አለቃ መቃብር



በቅዱስ ምድር ውስጥ ከሁሉም በላይ ታዋቂ የሆነው ይህ ህንጻ፣ በንጉስ ሄሮድስ የተገነባው አብርሐም ቤተሰብ መቃብር ቦታ እንዲሆን ገዝቶታል ተብሎ በባህል በሚ ታመንበት በእርሻ ባለ ድርብ ክፍል በሆነው ዋሻ ቦታ ላይ ነበር (ዘፍጥ. ፳፫)።

ታላቅ ድርጊቶች፥ የሣራ (ዘፍጥ. ፳፫) እና የአብርሐም (ዘፍጥ. ፳፭፡፱) መቃብር። ይስሐቅ፣ ርብቃ፣ እና ልያ በእዚህም ተቀብረዋል (ዘፍጥ. ፴፱፡፴–፴፩)። የያዕቆብ አስካሬን ከግብፅ ወደ ከነዓን መጥቶ በዋሻው ውስጥ ተቀ ብሯል (ዘፍጥ. ፶)።

6. የይሁዳ ተራራማው አገር



የይሁዳ ተራራማው አገር ፷፯ ኪሎ ሜትር ረጅም እና ፷፯ ኪሎ ሜትር የሚሰፋ ነው። አብዛኛው መሬት በድንጋይ የተሞላ እና ለማረስ አስቸጋሪ ነበር። ተራራዎቹ ፍሬያማ በሆኑ ምድሮች ባሉት ሸለቆዎች ይከፋፈላሉ። የመጀመሪያው እስራኤላውያን ከሚወሯቸው ለመጠበቅ በመጠቀም በእነዚህ ተራራዎች ውስጥ ይኖሩ ነበር።

ታላቅ ድርጊቶች፥ ጌታ ይህን ምድር ለአብርሐም እና ለዘሩ ቃል ገባ (ዘፍጥ. ፲፫፥፲፭–፲፰፤ ፲፯፥፰)። ሣራ እና አብርሐም በእርሻ ባለ ድርብ ክፍል በሆነው ዋሻ ቦታ፣ በኬብሮን ተቀበሩ (ዘፍጥ. ፳፫፥፲፤ ፳፭፥፱)። ዳዊት ኢየሩሳሌምን ከኢያቡሳውያን መልሶ ያዘ (፪ ሳሙ. ፭፥፮–፱)። ብዙ የብሉይ ኪዳን ድርጊቶች በእነዚህ ተራራዎች ላይ ከሌሎች ቦታዎች ሁሉ በላይ እንደተደረጉ ተመዝግበዋል።

7. ቤተ ልሔም



ይህ ፎቶ በፊት ለፊት የሚያዩትን በድንጋይ የተሞሉ ተራራዎችን እና የእረኞች ሜዳዎችን እያሳየ፣ ከኋላም የእዚህ ዘመን የቤተ ልሔም ከተማን ያሳያል።

ታላቅ ድርጊቶች፥ ራሔል ለእዚህ በሚቀርብ ቦታ ነበር የተቀበረችው (ዘፍጥ. ፴፭፡፲፯–፳)። ሩት እና ቦዔዝ በእዚህ ይኖሩ ነበር (ሩት ፩፡፲፱–፪፡፱)። ዳዊት በእዚህ ተወልዶ እና ንጉስ እንዲሆን ተቀብቶ ነበር (፩ ሳሙ. ፲፮፡፩–፲፫)። አዳኝ በእዚህ ተወልዶ እናም እረኞቹና ሰብአ ሰገል እርሱን አምልከውት ነበር (ማቴ. ፪፡፩–፲፩፣ ሉቃ. ፪፡፱–፲፯)። (ቅ.መ.መ. ቤተ ልሔም ተመልከቱ።)

8. ኢየሩሳሌም



ከኢየሩሳሌም አልፎ ወደ ሰሜን ሲመለከቱ። በፎቶው መካከለኛ ቦታ ላይ ያለው የአለት ክብ ጣራ ተብሎ የሚ ጠራው ጣራው በወርቅ የተሸፈነበት የእስላም የተቀደሰ ስፍራ ነው። በጥንት ጊዜ አይሁዶች እዚህ በነበረ ቤተ መቅደስ ያመልኩ ነበር። በአለት ክብ ጣራ አጠገብ ያለው ግድግዳ የጥንት የኢየሩሳሌም ከተማን ይከብባል። በግ ድግዳው በስተቀኝ በኩል፣ በፎቶው ውስጥ የማይታይ፣ የቄድሮን ሸለቆ አለ። ከእዚያም በሚርቅ በስተቀኝ በኩ ልም የደብረ ዘይት ተራራ አለ። ወደ ሰሜንም፣ ከአለት ክብ ጣራ አልፎ፣ ምናልባት ጎልጎታ ወይም ቀራንዮም ይገኝ ይሆናል።

ታላቅ ድርጊቶች፥ በጥንት ጊዜ ሰሌም ተብላ ትጠራ ነበር (መዝ. ፸፮፡፪)። አብርሐርም አስራት ለመልከ ጼዴቅ ከፈለ (ዘፍጥ. ፲፬፡፲፰–፳)። አብርሐም ይስሀቅን ለመሰ ዋት መጣ (ዘፍጥ. ፳፪፡፪–፲፬)። ዳዊት ኢየሩሳሌምን ከኢ ያቡሳውያን መልሶ ያዘ (፪ ሳሙ. ፭፡፩–፱)። ንጉስ ሰለሞን ቤተመቅደስን ሰራ (፩ ነገሥ. ፮–፯)። ሌሂ ወደ ቃል ኪዳን ምድር ለመሄድ ወጣ (፩ ኔፊ ፩፡፬፣ ፪)። አዳኝ አገለገለ፣ ለኃጢያት ዋጋ ከፈለ፣ እናም በትንሳኤ ተነሳ (ማቴ. ፳፩–፳፰)። አዳኝ እንደተነበየው፣ ኢየሩሳሌም ከሞተ ከትንሽ ጊዜ በኋላ ተደመሰሰች (ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፡፣–፳)። ኢየ ሩሳሌም በመጨረሻው ቀናት ትወረራለች (ሕዝ. ፴፰–፴፱፣ ኢዩ. ፪–፣ ራዕ. ፲፩፣ ፲፮)። እንደ ዳግም ምፅ ዓት ድርጊቱ አዳኝ ወደ እዚህ ይመጣል (ዘካ. ፲፪–፲፬፣ ት. እና ቃ. ፴፭፡፴፰–፴፣)። (ቅ.መ.መ. ኢየሩሳሌም፣ ሳሌም ተመልከቱ።)

9. የሄሮድስ ቤተመቅደስ



ይህ ፎቶ በ፳፯ ዓ.ም. ውስጥ ምን ይመስል እንደነበር የሚ ታሰብበትን የሄሮድስ ቤተመቅደስ ሞዴልን ያሳያል (፩፡፣ ፱ ቅርፊት ማመዛዘኛ)። የቤተመቅደሱ ግድግዳ የቅድስት ቅዱሳን የተቀደሰ ቦታ ያለውን ህንጻ፣ ቅዱስን ቦታን እና ሶስት ታላላቅ ቤተ መንግስቶችን የሚከብ ነበር።

ታላቅ ድርጊቶች፥ ዮሴፍ እና ማርያም ህጻኑን ኢየሱስ ወደ ቤተመቅደስ ወሰዱ (ሉቃ. ፪፡፣ ፳፪–፴፰)። አዳኝ በ፲፪ አመቱ በቤተመቅደስ ውስጥ አስተማረ (ሉቃ. ፪፡፣ ፵፩–፵፮)። አዳኝ ገንዘብ ለዋጮችን ከቤተመቅደስ አስወጣ (ማቴ. ፳፩፡፣ ፲፪–፲፫)፣ እና ስለቤተመቅደሱ መደ ምሰስ ተነበየ (ማቴ. ፳፬፡፣ ፩–፪)። በኢየሩሳሌም ወደፊት ቤተመቅደስ ይገነባል (ሕዝ. ፵–፵፰፣ ዘካ. ፲፡፣ ፲–፱)። (ቅ.መ.መ. ቤተመቅደስ፣ የጌታ ቤት ተመልከቱ።)

10. የቤተመቅደስ ደረጃዎች



የቤተመቅሱ ስፍራ በክፍሎች የተከፋፈለ ነበር፣ እናም የውጪው ክፍል በመሬት የሚገኘው የፎቅ ክፍል ነው። የሚያመልኩት ከበታች ወደ ውጪው ክፍል እና ከእዚያም ወደ ውስጠኛው ክፍል ከሚያስገቡት ከእነዚህ ደረጃዎች በተጨማሪ በተለያዩ በሮች ይገባሉ። ከእግዚአብሔር ልጅ በተጨማሪ፣ ብዙ ሺህ ሰዎች እነዚህን ደረጃዎች ወጥተውባቸዋል። የቲቶ ሰራዊት ቤተመቅደስን በ፸ ዓ.ም. ሲደመስሱት፣ ደረጃዎቹ በተሰባበሩ ነገሮች ተሸፍኖ ነበር። የድሮ የኢየሩሳሌም ከተማ የጥንታዊ ታሪክ በሚያጠኑ ሰዎች በ1970 (እ.አ.አ.) ተቆፍሮ በሚወጣበት ጊዜ እነዚህ ተገልጠው ነበር።

ታላቅ ድርጊቶች፥ ሕዝቅኤል የወደፊት ቤተመቅደስ ምን ያህል ሰፊ እንደሚሆን እና እንደሚመስል በራዕይ አየ (ሕዝ. ፵)። (ቅ.መ.መ. ቤተመቅደስ፣ የጌታ ቤት ተመ ልከቱ።)

11. ደብረ ዘይት ተራራ



ይህ ትእይንት በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ካለው የኦርሰን ሀይድ መናፈሻ ቦታ ወደ ደቡብ ምዕራብ የሚመለከት ነው። በደብረ ዘይት ተራራ በስተምእራብ ዳገት ላይ ጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ ይገኛል። በጥቅምት ፲፯ ቀን ፲፰፻፶፭ (እ.አ.አ.)፣ ሽመግሌ ኦርሰን ሀይድ በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ወጣ ወጡ እናም ለአብርሐም ልጆች እንደገና መመለስ እና ለቤተመቅደስ እንደገና መገንባት የትንቢት ጸሎት ቅዳሴ አቀረበ።

ታላቅ ድርጊቶች፣ አዳኝ አስቀድሞ እንደተናገረው፣ ሮሜ ኢየሩሳሌምን በ፷ ዓ.ም. ደመሰሰች (ጆ.ስ.—ማቴ. ፭፡፳፪ ተመልከቱ)። አዳኝ ለአለም በሙሉ ከመታየቱ በፊት በደብረ ዘይት ተራራ ላይ መቆሙ አይቀርም። (ዘካ. ፲፬፡፫–፭፣ ት. እና ቃ. ፵፭፡፵፰–፶፣ ፲፮፡፲–፲፩፣ ቅ.መ.መ. ደብረ ዘይት ተራራ ተመልከቱ።)

12. ጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ

ይህ የአረጀ የወይራ ዛፍ ፎቶ የተነሳው በባህል የጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ ነው ተብሎ በሚታመንበት ቦታ ነው። አዳኝ በተካደበት ቀን ከከፍተኛው ክፍል ወጥቶ በዚህ አጠገብ ጸለየ።

ታላቅ ድርጊቶች፥ በእዚህ ቦታ ክርስቶስ ለሰው ዘር ኃጢያቶች መሰቃየትን ጀመረ (ማቴ. ፳፮፤ ፴፪–፴፩፤ ማር. ፲፬፡ ፴፪–፴፮፤ ት. እና ቃ. ፲፱፡ ፲፯–፲፱)። ከጸሎቱ በኋላ በአስቆሮቱ ይሁዳ ተካደ፣ እናም በአትክልት ስፍራው ከተያዘ በኋላ ደቀመዛሙርቱ ለጊዜም ካዱት (ማር. ፲፬፡ ፶)። (ቅ.መ.መ. ጌቴሴማኒ ተመልከቱ።)

13. ጎልጎታ

ይህ የራስ ቅል የሚመስለው ከፍ ያለ ድንጋይ እናም በኢየሩሳሌም የደማስቆ በር ውጪ የሚገኝ ቦታ (ዮሐ. ፲፱፡፲፯፡፳)፣ የተሰለቀበት ጎልጎታ ይሆናል።

ታላቅ ድርጊቶች፥ ኢየሱስ ከተገረፈ እና ከተሳለቁበት በኋላ፣ "የራስ ቅል ስፍራ ወደሚሆን ጎልጎታ ወደሚባለው ስፍራ" ተወሰደ፣ በእዚያም ተሰቀለ (ማቴ. ፳፯፡፳፭–፴፭፣ ዮሐ. ፲፱፡፲፯–፲፰)። (ቅ.መ.መ. ጎልጎታ ተመል ከቱ።)

14. የአትክልት ስፍራ መቃብር



የአርማትያሱ ዮሴፍ መቃብር ይገኝበት ሊሆን የሚችል በት ቦታ። አንዳንድ የዚህ ዘመን ነቢያት የአዳኝ አስከ ሬን በዚህ መቃብር ውስጥ እንደተቀበረ ስሜት አላቸው።

ታላቅ ድርጊቶች፣ አዳኝ በመስቀል ላይ ከሞተ በኋላ፣ አስከሬኑ ከድንጋይ ተወቅሮ በተሰራ አዲስ መቃብር ውስጥ ተቀበረ (ማቴ. ፳፯፡፣ ፶፯–፷)። በሶስተኛው ቀን፣ ብዙ ሴቶች ወደ መቃብሩ ሄዱ እና የአዳኝ ሰውነት በእ ዚያ እንደሌለ አዩ (ማቴ. ፳፰፡ ፩፤ ዮሐ. ፳፡ ፩–፪)። ሐዋ ሪያቱ ጴጥሮስ እና ዮሐንስ ደግሞም ወደ መቃብሩ ሄዱ እና ሰውነቱ በእዚያ እንደሌለ አዩ (ዮሐ. ፳፡ ፪–፱)። ከሞት የተነሳው አዳኝ በመግደላዊት ማርያም ታየ (ዮሐ. ፳፡ ፲፩–፲፰)።

15. ኢያሪኮ



ይህ ፎቶ አሁን በኢያሪኮ የሚገኙትን ሳር ቅጠል ያሳያል። በጥንት ጊዜ በዮርዳኖስ ወንዝ ሸለቆ የሚገኝ በግምብ የተ ከበበች፣ ከባህር በ፪፻፶፪ ሜትር ዝቅ ያለች ከተማ ነበረች። ዘንባባ እና የቡርትካን ዛፎች በደንብ የሚያድጉበት የእርሻ ቦታ ነበረች። በኋላውም የባህል የፈተና ተራራ ይታያል (ማቴ. ፬፡ ፩–፲፩)።

ታላቅ ድርጊቶች፥ በእዚህ ቦታ አካባቢ፣ ኢያሱ እና የእ ስራኤል ልጆች ወደ ቃል ኪዳን ምድር በመግባት የዮር ዳኖስ ወንዝን ለመጀመሪያ ጊዜ ተሻገሩ (ኢያ. ፪፡ ፩–፫፣ ፫፡ ፲፬–፲፯)። ጌታ ግንቡ በእስራኤል ሰራዊት ፊት በተ አምራት እንዲወድቅ አደረገ (ኢያ. ፮፣ ደግሞም ዕብ. ፲፩፡ ፴ ተመልከቱ)። ኢያሱ በከተማዋ ላይ እርግማን ጣለ (ኢያ. ፮፡ ፳፮)፣ ይህም ተፈጸመ (፩ ነገሥ. ፲፮፡ ፴፬)። ኤልሳዕ የኢያሪኮን ውሀ ፈወሰ (፪ ነገሥ. ፪፡ ፲፰–፳፪) አዳኝ ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄድ፣ አይነ ስውር የሆነውን በርጤሜዎስን በመፈወስ እናም ከቀ ራጩ ዘኬዎስ ጋር በመቆየት፣ በዚህች ከተማ አለፈ (ማር. ፲፡ ፵፮–፶፪፣ ሉቃ. ፲፰፡ ፴፭–፵፫፣ ፲፱፡ ፩–፲)። በመልካሙ ሳምራዊ ምሳሌ ውስጥ ከኢያሪኮ ወደ ኢየ ሩሳሌም የሚወስደው መንገድ ተጠቅሷል (ሉቃ. ፲፡ ፴–፴፯)። (ቅ.መ.መ. ኢያሪኮ ተመልከቱ።)

16. ሴሎ



በእዚህ የምዕራብ ትእይንት፣ ከመሀከል ወደ ግራ በኩል ያለችው የጥንት ሴሎ ከተማ ፍራሽ ይታያል።

ታላቅ ድርጊቶች፥ የእስራኤል ጎሳዎች ተሰበሰቡ እናም የተመደቡላቸውን ክልል ተቀበሉ (ኢያ. ፲፰–፳፪)። ድንኳኑ እና ታቦቱ በእዚህ ተቀምጠው ነበር እና ለብዙ መቶ አመቶችም በእዚህ ቆዩ (ኢያ. ፲፰፡ ፩)። በእዚህም ሐና ጸለየች እናም ልጇን ሳሙኤልን ለጌታ አገልግሎት ቀደሰች (፩ ሳሙ. ፩)። እስራኤላውያን ታቦትን ከሴሎ ወሰዱ እናም ታቦቱን በያዙት በፍልስጤማውያን ተሸ ነፉ (፩ ሳሙ. ፬፡ ፩–፲፩)።

17. ሴኬም



የሴኬም የጥንት ቦታ። በፊት የሚታየው ገሪዛን ተራራ ነው፣ እናም ከዚያም በኋላ ጌባል ተራራ አለ። ሴኬም በእነዚህ ሁለት ተራራዎች መካከል ትገኛለች።

ታላቅ ድርጊቶች፥ አብርሐም በሴኬም ሰፈረ (ዘፍጥ. ፲፪፡ ፮–፯)። ያዕቆብ በእዚህ ሰፈረ እናም ቁራሽ መሬት ገዛ (ዘፍጥ. ፴፫፡ ፲፰–፳)። ገሪዛን ተራራ የበረከት ተራራ ሲሆን፣ ጌባል ተራራ የዕርግማን ተራራ ነው (ዘዳግ. ፳፯–፳፰)። በጌባል ተራራ ላይ፣ ኢያሱ የሙሴ ህግጋትን የያዘ ሀውልት ገነባ እና ከእዚያም በኋላ ህጉን ለእስራኤላው ያን አነበበ (ኢያ. ፰፡ ፴–፴፭)። የዮሴፍ አጥንቶች በሴኬም ተቀበሩ (ኢያ. ፳፬፡ ፴፪)።

18. ዶታይን በሰማርያ ውስጥ

ዶታይን በጉብታና በሸለቆ የሚታወቅ ነው። ይህም ለግጦሽ አመቺ መሬት ነው። እስራኤላውያን በምድሩ ሲሰፍሩ፣ ይህ ክልል ለምናሴ ተሰጥቶ ነበር።

ታላቅ ድርጊቶች፥ በዶታይን ሸለቆ፣ ዮሴፍ ወደ ግብፅ ተሸጠ (ዘፍጥ. ፴፯፥ ፲፪–፳፰)። ኤልዛቤል የእስራኤል ነቢያትን ለመግደል በሞከረችበት ጊዜ አብድዩ ብዙ መቶ ነቢያትን በዋሻ ውስጥ በመደበቅ አዳነ (፩ ነገሥ. ፲፰፥ ፲፫)። የሶርያ ሰራዊት ጌታ በተአምራት ያዳነውን ኤልሳዕን እና አገልጋዩን ከበቡ (፪ ነገሥ. ፮፥ ፲፫–፳፫)።

19. ቂሣርያ እና ከሼረን እስከ ቀርሜሎስ ያለው ሜዳ

ወደ ጥንት የባህር ወደብ ከተማ ወደሆነችው ቂሣርያ እና ከሼረን እስከ ቀርሜሎስ ያለው ሜዳ ወደ ሰሜን ይመለ ከታል። ደግሞም በፎቶው ወደ ላይ ሲመለከቱ ቀርሜሎስ ተራራዎች ይታያሉ።

ታላቅ ድርጊቶች፥ ኤልያስ የበአል የሀሰት ነቢያትን በቀር ሜሎስ ተራራ ላይ ተቃወመ (፩ ነገሥ. ፲፰)። በጥንት ጊዜ ዎች አስፈላጊ መንገድ የነበረው ቪያ ማሪስ (የባህር መን ገድ)፣ በቂሣርያ በስተምስራቅ በኩል ይገኛል። በኢዮጴ ከነበረው አስደናቂ ራዕይ በኋላ፣ ጴጥሮስ ቆርኔሌዎስ የሚ ባል የመቶ አለቃ በማስተማር በአህዛብ መካከል በቂሣር ያም መስበክ ጀመረ (የሐዋ. ፣)። ፊልጶስ በእዚህ ሰበከ፣ ኖረ፣ እናም የተነበዩ አራት ሴት ልጆች ነበሩት (የሐዋ. ፳፡፡ ፳፩፡ ፳፩–፳)። ጳውሎስ በከተማዋ ለሁለት አመት ውስጥ ታስሮ ነበር (የሐዋ. ፳፫–፳፭)። ለፊልክስ፣ ለፊስ ጦስ፣ እና “በጥቂት ክርስቲያን ልታደርገኝ” ነበር ላለው ለሄሮድስ አግሪጳ ሁለተኛ ሰበከ (የሐዋ. ፳፭፡ ፳፮)።

20. ኢዮጴ



ወደ ሰሜን በስተምዕራብ የወደብ ከተማ ወደ ሆነችው ወደ ኢዮጴ ትእይንት።

ታላቅ ድርጊቶች፥ ዮናስ ወደ ተርሴስ በመርከብ ለመ ሄድ ወደ ኢዮጴ ሄደ (ዮና. ፩፡፩–፫)። ኢዮጴ በመጀመ ሪያ ሰለሞን እና በኋላም ዘሩባቤል ከሊባኖስ የጥድ ዛፍ ጫካ ቤተመቅደሱ የሚገነባበት ሳንቃ ለማምጣት ይጠ ቀምበት የነበረ የባህር ወደብ ነበር (፪ ዜና ፪፡፲፮፤ ዕዝ. ፫፡፯)። በእዚህም ጴጥሮስ ዶርቃ ተብላ የምትታወቀውን ጣቢታን ወደ ህይወት መልሶ አስነሳ (የሐዋ. ፱፡፴፮–፵፫)። ጴጥሮስ ደግሞም በአህዛብ መካከል የመስበክ አስፈላጊ ነትን የሚገልፅለት ንጹህ እና እርኩስ የሆኑትን እንስሳት ራዕይ አየ (የሐዋ. ፲)። ኦርሰን ሀይድ በ፲፰፻፶፯ (እ.አ.አ.) ቅዱስ ምድርን ለመቀደስ በእዚህ ደረሱ።

21. ኢይዝራኤል ሸለቆ

ከታቦር ተራራ በላይ ወደ ኢይዝራኤል ሸለቆ፣ ደግሞም የእስድሬሎን ሜዳ ተብሎ ወደሚታወቀው፣ ወደ ደቡብ በስተምዕራብ የሚመለከት ትእይንት። ምንም እንኳን የኢይዝራኤል ሸለቆ በብዙ ጊዜ ከነበሩት ታላቅ ሸለቆዎች አንዱ እንደሆነ ቢታሰብበትም፣ ይህ የአኮ ሜዳን ከዮርዳ ኖስ ሸለቆ ጋር እና የገሊላ ባህርን ክልል ጋር የሚያገናኝ ተከታታይ ሸለቆዎች ነው። የመጊዶ ሸለቆ፣ ለምሳሌ፣ በእዚህ ሸለቆ በስተምዕራብ በኩል ነው። የኢይዝራኤል ሸለቆ በምዕራብ በሚገኘው ሜድትሬኒያን ባህር እና በምስራቅ በሚገኘው በዮርዳኖስ ሸለቆ መካከል ቅዱስ ምድርን የሚያልፍ ዋና መንገድ ነው።

ታላቅ ድርጊቶች፣ ግብፅን እና መስጴጦምያን የሚያገናኘው ታላቁ መንገድ በእዚህ ሸለቆ በኩል ያልፋል፣ እናም በእዚህም ብዙ ጦርነቶች ነበሩ (መሳ. ፩፡ ፳፩–፳፯፤ ፭፡ ፲፱፤ ፪ ነገሥ. ፳፫፡ ፳፱–፴)። ታላቁ የመጨረሻው ጦርነት በእዚህ ምድር የሚጀመረው በአርማጌዶን ጦርነት ነው፣ ይህም ከአዳኝ ዳግም ምፅዓት ከአጭር ጊዜ በፊት ይዋጉታል፤ ይህም ስያሜውን ከሀገር ማጌዶን ወይም የማጌዶን ተራራ የሚያገኝ ነው (ሕዝ. ፴፰፤ ኢዩ. ፫፡ ፱–፲፬፤ ዘካ. ፲፬፡ ፪–፭፤ ራዕ. ፲፮፡ ፲፬–፲፮)።

22. ታቦር ተራራ



ወደ ሰሜን በስተምስራቅ ወደ ታቦር ተራራ ትእይንት። የታቦር ተራራን የሚከብበው ምድር የኢይዝራኤል ሸለቆ ክፍል ነው፤ ደግሞም የእስድራሎን ሜዳ ተብሎ ይታወቃል። ናዝሬት ከታቦር ተራራ አጠገብ ከሚገኙ ኮረብታዎች ውስጥ ይገኛል።

ታላቅ ድርጊቶች፥ ዲቦራ እና ባርቅ የጌታን ሰራዊት በአሶር ንጉስ ኢያቢስን በመቃወም ሰበሰቡ (መሳ. ፬፡፡–፲፭)። የታቦር ተራራ አዳኝ ተቀየረበት ተብሎ በባህል ከሚታመንበት ቦታ አንዱ ነው (ማቴ. ፲፯፡፡–፱)፤ ሌላው የአርሞንዔም ተራራ ነው። (ቅ.መ.መ. መለወጥ ተመልከቱ።)

23. የገሊላ ባህር እና የታላቅ ደስታ ተራራ

ጨው የሌለው ሀይቅ ወደሆነው ገሊላ ባህር በሰሜን በስ ተምስራቅ በኩል የደቡብ ምስራቅ ትእይንት። በመካ ከል የሚታየው ኮረብታ በባህል የታላቅ ደስታ ተራራ ነው ተብሎ የሚታመንበት ነው። ቅፍርናሆም፣ ከፎቶው ውጪ በግራ በኩል ነው። ጥብርያዶስ ከምዕራብ ባህር ዳር ርቆ በደቡብ በኩል ይገኛል።

ታላቅ ድርጊቶች፥ አዳኝ አብዛኛውን የስጋዊ አገልግ ሎቱን ያሳለፈው በእዚህ ክልል ነው። በእዚህም አስራ ሁለቱን ሐዋሪያት ጠራ እናም ሾመ (ማቴ. ፱፡ ፲፰–፳፪፤ ፲፡ ፩–፬፤ ማር. ፩፡ ፲፮–፳፡ ፪፡ ፲፫–፲፱፤ ፫፡ ፯፣ ፲፫–፲፱፤ ሉቃ. ፭፡ ፩–፲፩)፣ የተራራ ስብከትን አስተማረ (ማቴ. ፭–፯)፣ እናም በምሳሌ አስተማረ (ማቴ. ፲፫፡ ፩–፶፪፤ ማር. ፬፡ ፩–፴፬)። የሚቀጥሉትን ተዓምራት ፈጸመ፥ ለምጻሞችን ፈወሰ (ማቴ. ፰፡ ፩–፬)፣ ማዕበልን ጸጥ አደ ረገ (ማቴ. ፰፡ ፳፫–፳፯)፣ ከወጣት ሰው ወደ እሪያዎች ገብተው በባህር የሰመጡት አጋንንትን አስወጣ (ማር. ፭፡ ፩–፲፭)፣ ፭ ሺህ እና ፬ ሺህ መገበ (ማቴ. ፲፬፡ ፲፬–፳፩፤ ፲፭፡ ፴፪–፴፰)፣ ደቀመዛሙርቱ መረባቸን እንዲጥሉ አዘ ዛቸው፣ በእዚህም ብዙ አሳዎች አጠመዱ (ሉቃ. ፭፡ ፩–፯)፣ ብዙ ሰዎች ፈወሰ (ማቴ. ፲፭፡ ፳፱–፴፩፤ ማር. ፫፡ ፯–፲፪)፣ እናም ከትንሳኤው በኋላ ደቀመዛሙርቱን ለማስ ተማር ታየ (ማር. ፲፮፡ ፳፯–፳፰፣ ፲፯፡ ፣ ዮሐ. ፳፩፡ ፩–፳፫)። (ቅ.መ.መ. ገሊላ ተመልከቱ።)

24. ቅፍርናሆም



ቅፍርናሆም፣ በገሊላ ባህር ዳር በሰሜን በኩል የሚገኘው የኢየሱስ የገሊላ አገልግሎት ዋና ቦታ ነው (ማቴ. ፱፡፩–፪፤ ማር. ፪፡፩–፫)። አስፈላጊ እና ውጤታማ የአሳ ማጥ መጃና የንግድ ዋና ቦታ የነበረችው፣ የአህዛብ እና የአይ ሁድ መኖሪያ ነበር። የመጀመሪያው መቶ አመት የህዝብ ብዛት ከ፯ ሺህ በላይ አልነበሩም። ቅፍርናሆም በለማ ቦታ ተከብቦ፣ የአስፈላጊ የንግድ መንገድ የሚገኝበት ነበር። የሮሜ ወታደሮች ገንዳ መታጠቢያ እና ማከማቻ ቦታዎ ችን በእዚህ ገነቡ። በእዚህ ቦታ ብዙ ተዓምራት ቢፈ ጸሙም፣ ህዝቡ የአዳኝን አገልግሎት አስወገዱ። ኢየ ሱስ ስለዚህ ከተማዋን ረገማት (ማቴ. ፲፩፡፳፣ ፳፫–፳፬)። ከጊዜ በኋላም፣ ቅፍርናሆም ተሰባበረች እናም በእዚያ የሚኖሩትም ወጥተው ሄዱ።

ታላቅ ድርጊቶች፡ ቅፍርናሆም የአዳኝ የእርሱ ከተማ ነበር ተብሎ ይታወቃል (ማቴ. ፱፡፩–፪፤ ማር. ፪፡፩–፫)። በእዚህ ቦታ ብዙ ተዓምራትሰራ። ለምሳሌ፣ ከመቶ አለቃ አገልጋይ (ሉቃ. ፯፡፩–፲)፣ ከጴጥሮስ አማች (ማር. ፩፡፳፱፤ ፳፱–፴፩)፣ በጣራ በኩል መኝታው ከወረደው ሽባ (ማር. ፪፡፩–፲፪)፣ እና እጁ ከሰለለች ሰው (ማቴ. ፲፪፡፱–፲፫) በተጨማሪ ብዙ ሰዎችን ፈወሰ (ማር. ፩፡፴፪–፴፬)። በዚህም ብዙ እርኩስ መንፈሶችን አስወጣ (ማር. ፩፡፳፭–፳፯፣ ፴፪–፴፬)፣ የኢያኢሮስ ሴት ልጅን ከሞት አስነሳ (ማቴ. ፱፡፲፰–፲፱፤ ፳፫–፳፭፤ ማር. ፭፡፳፪–፳፬፣ ፴፭–፴፫)፣ እና በቅፍርናሆም ምኩራብ የህይወት-እንጀራ የሚለውን ስብከትን ሰጠ (ዮሐ. ፮፡፳፬–፶፱)። አዳኝ ጴጥ ሮስን ከገሊላ ባህር አሳ እንዲያጠምድ፣ አፉን እንዲከ ፍት፣ እና ቀረጥ የሚከፍልበት ሳንቲም እንዲያገኝ አዘ ዘው (ማቴ. ፲፯፡፳–፳፯)።

25. የዮርዳኖስ ወንዝ

የዮርዳኖስ ወንዝ በሰሜን በገሊላ ባህር ጀምሮ ወደ እዚህ ይፈሳሉ፣ እና ከእዚያም ወደ ሙት ባህር ይቀጥላል። ይህ ፎቶ የተነሳው ወንዙ ወደ ገሊላ ባህር በሚገባበት አጠገብ ነበር።

ታላቅ ድርጊቶች፥ ሎጥ የዮርዳኖስን ሜዳ ለእራሱ መረጠ (ዘፍጥ. ፲፫፡፣ ፲–፲፩)። ኢያሱ እስራኤላውያን ወደ ቃል ኪዳን ምድር እንዲሻገሩ ውሀውን ከፈለ (ኢያ. ፫፡፣ ፲፫–፲፯፣ ፬፡፩–፱፣ ፭–፯፬)። ኤልያስ እና ኤልሳዕ ውሀውን ከፈሉ (፪ ነገሥ. ፪፡፣ ፭–፰፣ ፲፪–፲፬)። ናዕማን ከለምጽ ደዌ ተፈውሶ ነበር (፪ ነገሥ. ፭፡፩–፲፭)። መጥምቁ ዮሐንስ ከአዳኝ በተጨማሪ ብዙ ሰዎች አጠመቀ (ማቴ. ፫፡፩–፮፣ ፲፫–፲፯)። (ቅ.መ.መ. የዮርዳኖስ ወንዝ ተመልከቱ።)

26. ፊልጵስ ቂሣርያ



ፊልጵስ ቂሣርያ የሚገኘው በአርሞንዔም ተራራ ነው። ይህ ምንጭ ከዮርዳኖስ ወንዝ ምንጭ አንዱ ነው። ይህን አካባቢ የሚገዛው ሄሮድስ ፊልጵስ ቂሥርያኑን እና እራሱን ለማክበር በእዚህ ቦታ ከተማ ገነባ፤ ከእዚህ በፊት ከተማው ጳኒያስ ተብሎ ይጠራ ነበር እና አሁን ባኒያስ ወይም ፊልጵስ ቂሣርያ ተብሎ ይጠራል።

ታላቅ ድርጊቶች፥ አዳኝ ከደቀመዛሙርቱ ጋር በፊልጵስ ቂሣርያ ተገናኘ። በእዚህም ጴጥሮስ አዳኝ "ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ" ነው ብሎ አወጀ። አዳኝም ለጴጥሮስ "የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ" ብሎ ቃል ገባለት (ማቴ. ፲፮፥ ፲፫–፳)።

27. ናዝሬት

ወደ ሰሜን ወደ ናዝሬት ከተማ የሚመለከት ትእይንት። ናዝሬት በመፅሐፍ ቅዱስ ዘመን ትንሽ መንደር ነው።

ታላቅ ድርጊቶች፥ ኔፊ በራዕይ የአዳኝን እናት በናዝሬት አያት (፩ ኔፊ ፲፩፡፲፫–፳፪)። መላእኩ ገብርኤል ማር ያምን አዳኝን እንደምትወልድ ነገራት (ሉቃ. ፩፡፳፮–፴፭)። ገብርኤል ዮሴፍ ማርያምን እንዲያገባና ልጁን ኢየሱስ ብሎ ስም እንዲሰጠው ነገረው (ማቴ. ፩፡፲፰–፳፭)። ኢየሱስ በናዝሬት አደገ (ማቴ. ፪፡፲፱–፳፫፤ ሉቃ. ፪፡፩–፵፣ ፬፡፲፮)። በምኩራብ ውስጥ ሰበከ እናም መሲህ እንደሆነ አወጀ (ሉቃ. ፬፡፲፮–፳፭)፣ ነገር ግን የናዝሬት ሰዎች አስወገዱት (ማቴ. ፲፫፡፶፭–፶፰፤ ሉቃ. ፬፡፳፭–፴)። (ቅ.መ.መ. ናዝሬት ተመልከቱ።)

28. ዳን

እስራኤላውያን ምድሯ ከማሸነፋቸው በፊት፣ ሌሼም (ኢያ. ፲፱፡፵፯) ወይም ሌሳ (መሳ. ፲፰፡፯፣ ፲፬) ተብላ የምትጠራ የጥንት የዳን ከተማ። በእዚህ ቦታ የሚገኙት ምንጮች፣ በፊልጵስ ቂሣርያ ከሚገኙት ምንጮች ጋር የዮርዳኖስ ወንዝ ዋና መንጮች ናቸው።

ታላቅ ድርጊቶች፣ አብርሐም ሎጥን አዳነ (ዘፍጥ. ፲፬፡፲፫–፲፮)። የዳን ጎሳዎች ይህን ክልል አሸንፈው ያዙ እናም ዳን ብለው ጠሩት (ኢያ. ፲፱፡፵፯–፵፰)። ኢዮርብዓም ለሰሜን አስር ጎሳዎች መውደቅ ምክንያት የነበረውን የወርቅ ጥጃ ያለው የሀሰት ቤተመቅደስ ሰራ (፩ ነገሥ. ፲፪፡፳፱–፴፫)። ዳን የእስራኤል የሰሜን ከተማ ነው—በዚህም ምክንያት ነው ቅዱሳት መጻህፍት ስለእ ስራኤል ምድር “ከቤርሳቤህ እስከ ዳን ድረስ” ብለው ይጠቅሷት ነበር (፪ ዜና ፴፡፭፣ ቤርሳቤህ በደቡብ ጫፍ የምትገኝ ከተማ ነበረች)። (ቅ.መ.መ. ዳን ተመልከቱ።)

29. አቴና

ከአርዮስፋጎስ (ማርስ ኮረብታ) የተነሳው ይህ ፎቶ በአቴና ውስጥ የተለያዩ ጣዖቶች ማምለኪያ የሚገኝበት የፓርቴኖን ፍራሽ ያሳያል። አቴና የጥንት ግሪክ አቲካ ዋና ከተማ እናም በአዲስ ኪዳን ጊዜዎች ውስጥ የሮሜ የአካይያ ክልል ነበረች። ስሟም የተሰጣት የግሪክ ሴት ጣዖት አቴናን ለማክበር ነበር። በአዲስ ኪዳን ጊዜዎች፣ አቴና የድሮ ታላቅነቷን እና ክብሯን አጥታ ነበር፣ ነገር ግን "ከማይታወቅ አምላክ" በተጨማሪ፣ የብዙ ወንድ እና ሴት ጣዖቶች ሀውልቶች እና ቅርሶች ነበሯት (የሐዋ. ፲፯፡ ፳፫)።

ታላቅ ድርጊቶች፥ ሐዋሪያው ጳውሎስ ከተማዋን ጎበኘ እናም በማርስ ኮረብታ ላይ ቆሞ "ስለማይታወቅ አምላክ" ሰበከ (የሐዋ. ፲፯፡ ፲፭–፴፬)። ሚስዮኖች ከአቴና ወደ ሌሎች የክሪክ ክፍሎች ተልከው ነበር (፩ ተሰ. ፫፡ ፩–፪)።

30. ቆሮንቶስ



ቆሮንቶስ የሮሜ ክልል አካይያ ዋና ከተማ ነበረች። ፔሎፖኑሰን ከግሪክ ምድር ጋር በሚያገናኝ በምስራቅ እና በምዕራብ በኩል ወደብ ያለው ባህረ ሰላጤ ላይ የም ትገኝ ነበረች። የሀብት እና ተፅዕኖ የሚገኝበት የወደብ ከተማ ነበረች።

ታላቅ ድርጊቶች፥ ጳውሎስ ለአንድ አመት ከስድስት ወር በቆሮንቶስ ኖረ እና በእዚህ ቤተክርስቲያኗን መሰረተ (የሐዋ. ፲፰፡፩–፲፰)። ጳውሎስ በቆሮንቶስ አካባቢ ውስጥ ላሉት አባላት ብዙ ደብዳቤዎች ጻፈ፣ ሁለቱም አሁን በአ ዲስ ኪዳን ውስጥ ናቸው (፩ እና ፪ ቆሮንቶስ)። ለሮሜ የተ ጻፈው ደብዳቤ ከቆሮንቶስ የተጻፈ ሳይሆን አይቀርም።

31. ኤፌሶን

ሐዋሪያው ጳውሎስ የሰበከበት በኤፌሶን የሚገኝ የግሪክ ቤተ ተውኔት ፍራሽ። በአዲስ ኪዳን ዘመናት፣ ኤፌሶን ለሮሜ ሴት ጣዖት አርጤምስ ክብር በተገነባው አስደናቂ መቅደስ ምክንያት በጣም ታዋቂ ነበረች። አሁን የፈረሰች ብትሆንም፣ ኤፌሶን በእስያ ውስጥ ያለው የሮሜ ክፍለ-ሀገር ዋና ከተማ እና የንግድ ቦታ ነበረች። የከተማው የብር አንጣሪዎች የአርጤምስ ምስልን በመሸጥ ጥሩ ንግድን መስርተው ነበር።

ታላቅ ድርጊቶች፥ ሐዋርያው ጳውሎስ በሁለተኛው የሚስዮን ጉዞው መጨረሻ ላይ ኤፌሶንን ጎበኘ (የሐዋ. ፲፰፡፲፰–፲፱)። በሶስተኛው ጉዞው በከተማዋ ለሶስት አመት ቆየ። ከከተማዋ በግድ እንዲወጣ የተደረገው ጳውሎስ የሀሰት ጣዖት የሆነችውን አርጤምስ ማምለክን በመቃወም በመስበኩ ምክንያት የብር አንጣሪዎች ንግድ እያጡ ስለነበር ነው (የሐዋ. ፲፱፡፩፣ ፲፣ ፳፫–፳፩፣ ፳፡፩)። የኤፌሶን ቤተ ተውኔት በግሪኮች ከተሰሩት ሁሉ በላይ ትልቅ እናም የጳውሎስ ጓደኞች በአመጽ የተነሱትን የተቋቋመበት ቦታ ነበር (የሐዋ. ፲፱፡፳፱–፴፩)። ጳውሎስ በኤፌሶን ለነበሩት የቤተክርስቲያኗ አባላት በሮሜ እስር ቤት ውስጥ እያለ መልእክት ጻፈላቸው። በዮሐንስ ራዕይ ውስጥ የተጠቀሰው በእስያ ካሉት የቤተክርስቲያኗ ቅርንጫፎች አንዱ የሚገኘው በኤፌሶን ውስጥ ነው (ራዕ. ፩፡፲–፲፩፣ ፪፡፩)።

32. የፍጥሞ ደሴት



በአጂየን ባህር ላይ የምትገኝ እና ዮሐንስ የተወገደበት ደሴት ፍጥሞ (ራዕ. ፩፡፱)። በባህል መሰረት፣ በዕብነ በረድ የድንጋይ ካብ ውስጥ ይሰራ ነበር።

ታላቅ ድርጊቶች፡ ዮሐንስ አፖክሊፕስ (ደግሞም የዮሐንስ ራዕይ) ተብሎ የሚጠራውን ራዕይ አየ። ጌታ በእስያ ለሚገኙት ሰባት ቤተክርስቲያናት እንዲልክ ነገረው (ራዕ. ፩፡፲፩)።

የቤተክርስቲያኗ ታሪክ ካርታዎች

የሚቀጥሉት ካርታዎች የኋለኛው ቀን ቅዱሳን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን የመጀመሪያ ታሪክን እና በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ እና እርሱን በሚከተሉት በኩል የተሰጡትን ቅዱሳት መጻህፍት በደንብ ለመረዳት እንድትችሉ ይረዷችኋል። በቅዱሳት መጻህፍት ውስጥ የሚወያዩትን የምድሩ ጂኦግራፊ በማወቅ፣ የቅዱሳት መጻህፍት ድርጊቶችን በደንብ ለመረዳት ትችላላችሁ።

ማጠቃለያና ቁልፎች

ከእዚህ በላይ ያሉት ካርታዎች ዋና ሀሳቦች የሚቀጥሉት ቁጥር የተሰጣቸውን ካርታዎች ላይ የሚያተኩር ናቸው። እነዚህ ካርታዎች ታላቅ ክፍለ አገሮችን እና በመልክአ ምድራዊ አካባቢዎች ላይ የሚያተኩሩ ናቸው።

1. የሰሜን ምስራቅ ዩናይትድ ስቴትስ
2. ፓልማይራ-ማንቸስተር፣ ኒው ዮርክ፣ ፤ ፤ ፤–፤ ፤ ፤
3. የኒው ዮርክ፣ የፔንስልቬኒያ፣ እና የኦሀዮ፣ ዩ.ኤስ.ኤ. አካባቢ
4. ከርትላንድ፣ ኦሀዮ፣ ፤ ፤ ፤–፤ ፤ ፤
5. የምዙሪ፣ የኢሊኖይ፣ እና የአየዋ አካባቢ፣ ዩ.ኤስ.ኤ.
6. የቤተክርስቲያኗ ወደ ምዕራብ ጉዞ
7. የአለም ካርታ



የሚቀጥለው በካርታዎች ላይ የሚጠቀሙባቸውን የተለያዩ ምልክቶች እና ልዩ የፊደል አጣጣሎች ልትረዱበት የምትችሉበት ቁልፍ ነው። በተጨማሪም፣ እያንዳንዱ ካርታዎች ስለአንዱ ካርታ ተጨማሪ ምልክቶች መግለጫ ይኖራቸዋል።

■ የቡርትካን ቀለም ያለው አራት ማዕዘን ህንጻዎችን፣ የንግድ ቦታዎችን፣ እና ሌሎች የከተማ መልኮችን ያመለክታል።

● ቀይ ነጥብ ከተማን ያመለክታል።

የአትላንቲክ ውቅያኖስ ይህ ልዩ የፊደል አጣጣል አብዛኛውን ጊዜ የስነ መልክአ ምድር ቦታን፣ ለምሳሌ ሀይቆችን፣ ወንዞችን፣ ተራራዎችን፣ ሸለቆዎችን፣ በረሀዎችን፣ እና ደሴቶችን፣ ለማመልከት ይጠቀሙበታል።

ፓልማይራ ይህ ልዩ የፊደል አጣጣል ከተማዎችን ለመጠቆም ይጠቀሙበታል።

ኒው ዮርክ ይህ ልዩ የፊደል አጣጣል እንደ ክልሎች አይነት ትንሽ የፖለቲካ ክፍሎችን እና የዩ.ኤስ. ስቴቶች እና ግዛቶችን ለመጠቆም ይጠቀሙበታል።

ካነዳ ይህ ልዩ የፊደል አጣጣል እንደ ህዝቦች፣ አገሮች፣ እና ክፍለ አህጉሮች አይነት ትልቅ የፖለቲካ ክፍሎችን ለመጠቆም ይጠቀሙበታል።

1. የሰሜን ምስራቅ ዩናይትድ ስቴትስ



1. ቶፕስፊልድ ጆሴፍ ስሚዝ፣ ቀዳማዊ የተወለዱበት ቦታ፣ በ ሐምሌ ፲፪፣ ፲፯፻፹፩ (እ.አ.አ.) ተወለዱ።
2. ጊልሰም ሉሲ ማክ የተወለዱበት ቦታ፣ በሐምሌ ፰፣ ፲፯፻፹፯ (እ.አ.አ.) ተወለዱ።
3. ተርንብሪጅ ጆሴፍ ስሚዝ፣ ቀዳማዊ እና ሉሲ ማክ በዚህ ተጋቡ፣ ጥር ፳፬፣ ፲፯፻፹፯ (እ.አ.አ.)።
4. ዊትንግሀም ብሪገም ያንግ የተወለዱበት ቦታ፣ በሰኔ ፩፣ ፲፰፻፩ (እ.አ.አ.) ተወለዱ።
5. ሀርመኒ ኤማ ሄል በሀርመኒ ከተማ ተወልዳ ነበር፣ ሰኔ ፲፣ ፲፰፻፱ (እ.አ.አ.)።
6. ሼረን ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ በእዚህ ቦታ ተወለደ፣ ታህሳስ ፳፫፣ ፲፰፻፭ (እ.አ.አ.) (ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፫፣ ፫ን ተመልከቱ)።
7. ለበኖን የስሚዝ ቤተሰብ በለበኖን ከተማ ውስጥ ከ፲፰፻፲፩ እስከ ፲፰፻፲፫ (እ.አ.አ.) ድረስ ኖሩ፣ በዚህም ጊዜ ጆሴፍ ስሚዝ የተከታተሉ የእግር ቀዶ ጥገና ነበረው።
8. ኖርዊች የስሚዝ ቤተሰብ ከፖልማይራ ከመውጣታቸው በፊት ከ፲፰፻፲፩ እስከ ፲፰፻፲፯ (እ.አ.አ.) ድረስ በእዚህ ቦታ ኖሩ።
9. ፖልማይራ የስሚዝ ቤተሰብ በ፲፰፻፲፯ (እ.አ.አ.) ወደ እዚህ ከተማ መጡ (ጆ.ስ.—ታ. ፩፡፫)።

2. ፓልማይራ-ማንቸስተር፣ ኒው ዮርክ፣ ፲፰፻፸፭–፲፰፻፹፭



1. **የጆሴፍ ስሚዝ ቀዳማዊ በፍልጥ እንጨት የተሰራ ቤት** መልአኩ ሞሮኒ በመስከረም ፳፩–፳፪፣ ፲፰፻፳፫ (እ.አ.አ.) በእዚህ ቤት ክፍል ውስጥ በጆሴፍ ስሚዝ ታየ (ጆ.ስ.—ታ ፩፡፳፩–፳፯ን ተመልከቱ)።
2. **የጆሴፍ ስሚዝ ቀዳማዊ የእርሻ ቦታ** ይህ የ፳፯ ሄክታር የእርሻ ቦታ ከ፲፰፻፳ እስከ ፲፰፻፳፱ (እ.አ.አ.) ድረስ በስ ሚዝ ቤተሰብ ተሸሽሎ ነበር።
3. **ቅዱስ ጥሻ** በ፲፰፻፳ (እ.አ.አ.) ጸደይ መጀመሪያ በስ ሚዝ እርሻ ውስጥ በሚገኝ ጫካ ውስጥ የጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ የመጀመሪያ ራዕይ ደረሰ (ጆ.ስ.—ታ ፩፡ ፲፩–፳ን ተመልከቱ)።
4. **የጆሴፍ ስሚዝ ቀዳማዊ ቤት** ይህ ቤት መገንባት የተጀ መረው በ፲፰፻፳፪ (እ.አ.አ.) በአልቭን ስሚዝ ነበር እናም የስሚዝ ቤተሰብ ከ፲፰፻፳፭ እስከ ፲፰፻፳፱ (እ.አ.አ.) ድረስ ይኖሩበት ነበር።
5. **የከሞራ ኮረብታ** በመስከረም ፳፪፣ ፲፰፻፳፭ (እ.አ.አ.) መልአኩ ሞሮኒ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የወርቅ ሰሌዳዎ ችን ቤዚህ ቦታ (ጆ.ስ.—ታ. ፩፡ ፱–፴፡ ፴፱)።
6. **የማርቲን ሀሪስ የእርሻ ቦታ** ይህ የእርሻ ቦታ መፅሐፈ ሞርሞንን ለማተም በብድር ተይዞ እናም የአካባቢው ክፍልም ተሽጦ ነበር።
7. **ኢ. ቢ. ግራንዲን የማተሚያ ሱቅ** ፲ ሺህ መፅሐፈ ሞርሞን በዚህ ቦታ በ፲፰፻፳፱–፲፰፻፴ (እ.አ.አ.) ታተ መው ነበር።
8. **ሀተዊይ ብሩክ** በዚህ በመጀመሪያ በሚኖሩት በአብ ዛኛው ጊዜ ክሩክድ ክሪክ ተብሎ በሚታወቀው በዚህ ጅረት ውስጥ አንዳንድ የመጀመሪያ የቤተክርስቲያኗ ጥምቀቶች ተከናውነው ነበር።

3. የኒው ዮርክ፣ የፔንስልቬኒያ፣ እና የኦሀዮ፣ የ.ኤስ.ኤ. አካባቢ



1. **ሳውዝ ቤይንብርጅ** ጆሴፍ ስሚዝ እና ኤማ ሄል በጥር ፲፰፣ ፲፰፻፳፯ (እ.አ.አ.) ተጋቡ (ጆ.ስ.—ታ. ፩፡ ፣ ፣)።
2. **ኮልስቪል** በ፲፰፻፴ (እ.አ.አ.) የቤተክርስቲያኗ የመጀመሪያ ቅርንጫፍ በጆሴፍ ናይት ታላቁ ቤት ውስጥ ተደራጀ።
3. **በሀርመኒ ውስጥ የጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ ቤት** አብዛኛው የመፅሐፈ ሞርሞን ትርጉም የተፈጸመው በዚህ ቦታ ነበር። የክህነት ስልጣን በ፲፰፻፳፰ (እ.አ.አ.) በዳግም የተመለሰው በዚህ አካባቢ ነው (ት. እና ቃ. ፲፫፣ ፲፰፻፳፡ ፣ ጆ.ስ.—ታ. ፩፡ ፳፩–፳፪ ተመልከቱ)።
4. **ፊየት** ሶስቱ ምስክሮች የወርቅ ሰሌዳዎችን እና መልአክ ሞሮኒን በዚህ አዩ (ት. እና ቃ. ፲፯)። የመፅሐፈ ሞርሞን ትርጉን በሰኔ ፲፰፻፳፰ (እ.አ.አ.) በእዚህ ቦታ ተፈጸመ። በኢሪ መስኖ በኩል እና በእሪ ሀይቅ ወደ ከትርላንድ ኦሀዮ በሚያዝያና ግንቦት ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.) ተሰደዱ።
5. **ሜንዶን** የብሪገም ያንግ እና የሒበር ሲ. ኪምባል የመጀመሪያ ቤት።
6. **ከርትላንድ** በ፲፰፻፴ (እ.አ.አ.) ወደ ላማናውያን የተላኩት ሚስዮኖች በእዚህ ቦታ አለፉ እናም በከርትላንድ አካባቢ ስድኒ ሪግዶንን እና ሌሎችን አጠመቁ። ይህም ከ፲፰፻፴፩ እስከ ፲፰፻፴፰ (እ.አ.አ.) ድረስ የቤተክርስቲያኗ ጠቅላይ መምሪያ ቦታ ነበር። የዚህ ዘመን የመጀመሪያው ቤተመ ቅደስ የተገናባው በእዚህ ቦታ ነበር እናም በመጋቢት ፳፯፣ ፲፰፻፴፯ (እ.አ.አ.) ተቀደሰ (ት. እና ቃ. ፻፲፯ ተመልከቱ)።
7. **የኢሪ መስኖ** በኒው ዮርክ (ኮልስቪል፣ ፊየት፣ እና ማንቸስ ተር) ውስጥ የሚገኙት ሶስት የቤተክርስቲያኗ ቅርንጫፎች
8. **ሀይረም** ጆሴፍ እና ኤማ ከመስከረም ፲፰፻፴፩ እስከ መስ ከረም ፲፰፻፴፪ (እ.አ.አ.) ድረስ በእዚህ ቦታ ይኖሩ ነበር። ጆሴፍ እና ስድኒ ሪግዶን በመፅሐፍ ቅዱስ የጆሴፍ ስሚዝ ትርጉም (ጆ.ስ.ት.) ላይ ይሰሩ ነበር። የተቀበሉት ራዕይ እነ ዚህ ነበሩ፡ ት. እና ቃ. ፩፡ ፳፭–፳፩፣ ፳፫፣ ፳፡–፳፯፣ ፳፡–፳፫፣ ፳፡–፳፭፣ ፻፲፩፣ ፻፴፫፡
9. **አምኸርስት** በጥር ፳፭፣ ፲፰፻፴፪ (እ.አ.አ.) ጆሴፍ ስሚዝ እንደ ታላቅ ክህነት ፕሬዘደንት ተሾመ (ት. እና ቃ. ፳፭ን ተመልከቱ)።
10. **ቶራንቶ** የቤተክርስቲያኗ ሶስተኛው ፕሬዘደንት ጆን ቴይለር እና የሀይረም ስሚዝ ባለቤት ሜሪ ፊልዲንግ ስሚዝ ቤት።

4. ከርትላንድ፣ ኦሀዮ፣ ፲፯፻፱–፲፯፻፹፯



1. **ኒውል ኬ ዊትኒ ቤት** ጆሴፍ እና ኤማ በ፲፯፻፹፩ (እ.አ.አ.) ወደ ከርትላንድ ለመጀመሪያ ከመጡ በኋላ በዚህ ቦታ ለብዙ ሳምንታት ኖሩ። ጆሴፍ ብዙ ራዕዮችን በዚህ ቦታ ተቀበለ።
2. **የአይዝክ ሞርሲ የእርሻ ቦታ** ከመጋቢት እስከ መስከረም ፲፯፻፹፩ (እ.አ.አ.) ጆሴፍ እና ኤማ ስሚዝ በእዚህ ቦታ ይኖሩ ነበር። የመጀመሪያው ሊቀ ካህናት በእዚህ ቦታ ተሹመው ነበር። ጆሴፍ በጆሴፍ ስሚዝ የመፅሐፍ ቅዱስ ትርጉም (ጆ.ስ.ት.) ላይ ይሰራ ነበር።
3. **ኒውል ኬ ዊትኒ የንግድ ቤት** የቤተክርስቲያኗ ቀዳሚ አመራር የመንግስት ቁልፎች የተሰጣቸው በእዚህ ቦታ ነበር። በ፲፯፹፫ (እ.አ.አ.) ክረምት የነቢያት ትምህርት ቤትም እዚህ ቦታ ውስጥ ተሰበሰቡ። በ፲፯፹፫ (እ.አ.አ.) ጆ.ስ.ት. በእዚህ ቦታ እየተፈጸመ ነበር። ጆሴፍ እና ኤማ ከ፲፯፹፭ እስከ ፲፯፹፫ (እ.አ.አ.) ድረስ በእዚህ ቦታ ኖሩ። ጆሴፍ ብዙ ራዕዮች በእዚህ ቦታ ተቀበሎ ነበር።
4. **የጆንሰን ሆቴል** ሆቴሉ በከርትላንድ ከነበረው የእትመት ቢሮ የመጀመሪያው ያለበት ነበር። በጃክሰን ክፍለ አገር ምዙሪ ውስጥ የነበረው ማተሚያ ከተሰበረ በኋላ *The Evening and the Morning Star* በእዚህ ቦታ ታትመው ነበር። አስራ ሁለቱ ሐዋሪያት በግንቦት ፬፣ ፲፯፹፭ (እ.አ.አ.) ወደ መጀመሪያው ሚስዮናቸው ከእዚህ ቦታ ሄደው ነበር።
5. **የጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ ቤት** ጆሴፍ እና ኤማ ከ፲፯፹፩ እስከ ፲፯፹፭ መጀመሪያ (እ.አ.አ.) ድረስ በእዚህ ቦታ ኖሩ። የመፅሐፈ አብርሐም ትርጉም ተፈጽሞ ነበር እና ጆሴፍ በዚህ ቦታ ብዙ ራዕዮች ተቀብሎ ነበር።
6. **የእትመት ቢሮ** *Lectures on Faith* (የእምነት ንግግሮች) የተሰጠው በእዚህ ህንጻ ውስጥ ነበር። የአስራ ሁለቱ ሐዋሪያት እና የሰባዎች የመጀመሪያ ቡድን በእዚህም ቦታ ተጠርተውና ተሹመው ነበር። ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች (፩ኛው ቅጂ)፣ መፅሐፈ ሞርሞን (፪ኛው ቅጂ)፣ *The Evening and the Morning Star*፣ *Latter Day Saints' Messenger and Advocate*፣ እና *Elders' Journal* የመጀመሪያው እትም በእዚህ ቦታ ታትመው ነበር።
7. **የከርትላንድ ቤተመቅደስ** ይህ የዚህ ዘመን የመጀመሪያ ቤተ መቅደስ ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ መጥቶ ቤተመቅደሱን ተቀበለ። ሙሴ፣ ኤልያ፣ እና ኤልያስ መጡ እናም አንዳንድ የክህነት ስልጣን ቁልፎችን በዳግም መለሱ (ት. እና ቃ. ፲፲)። ደግሞም የነቢያት ትምህርት ቤት በእዚህ ቦታ ተገናኙ። በእዚህ የተቀበላቸው ራዕይ እነዚህ ነበሩ፥ ት. እና ቃ. ፲፱–፲፲፣ ፲፴፯።

   ከርትላንድ በነህሴ ፲፯፣ ፲፯፹፭ (እ.አ.አ.)፣ ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች እንደ ቅዱሳት መጻህፍት ተቀባይነት አገኙ። በከርትላንድ የተቀበላቸው ራዕዮች ት. እና ቃ. ፵፩–፵፣ ፵፪–፵፭፣ ፵፰–፵፱፣ ፷–፷፪፣ ፷፭–፷፱፣ ፸–፸፪፣ ፸፭–፸፱፣ ፹–፹፪፣ ፹፭–፹፱፣ ፺–፺፪፣ ፺፭–፺፱፣ ፻–፻፪፣ ፻፭–፻፱፣ ፻፴፩፣ እና ፻፴፯ ነበሩ። ክፍል ፲፱ አንዳንድ ንብረቶች በመተባበር ስርዓት ለሚሳተፉት የቤተክርስቲያን አባላት እንደ መጋቢነት እንዲሰጥ መደበ (ቁጥሮች ፲፱–፴፯ን ተመልከቱ)።

5. የምዙሪ፣ የኢሊኖይ፣ እና የአየዋ አካባቢ፣ ዩ.ኤስ.ኤ.



1. ኢንዲፔንደንስ የፅዮን ዋና ቦታን ይጠቁማል (ት. እና ቃ. ፻፯፡፫ን ተመልከቱ)። የቤተመቅደስ ቦታ በነሀሴ ፫፡ ፲፰፻፴፭ (እ.አ.አ.) ተቀድሶ ነበር። ቅዱሳን ከጃክሰን ክፍለ አገር በ፲፰፻፴፫ (እ.አ.አ.) ተሰድደው ነበር።
2. ፊሺንግ ወንዝ ጆሴፍ ስሚዝ እና የፅዮን ስፍራ የጃክሰን ክፍለ አገር ቅዱሳንን ወደ መሬታቸው ለመመለስ ከከርትላንድ ኦሀዮ ወደ ምዙሪ በ፲፰፻፴፱ (እ.አ.አ.) ተጓዙ። ት. እና ቃ. ፻፭ በእዚህ ወንዝ ዳር ነበር የተገለጸው።
3. ፋር ዌስት ይህ በምዙሪ ውስጥ ከነበሩት የሞርሞን መስፈሪያ ቦታ ትልቁ ነበር። በዚህም ቦታ የቤተመቅደስ መገንቢያ ቦታ ተቀድሶ ነበር (ት. እና ቃ. ፻፲፭ን ተመልከቱ)። በሐምሌ ፰፡ ፲፰፻፴፰ (እ.አ.አ.) በዚህ ቦታ፣ የአስራ ሁለቱ ሐዋሪያት ቡድን በብሪታንያ ደሴት በሚሰዮን እንዲያገለግሉ ከጌታ ጥሪ ተቀበሉ (ት. እና ቃ. ፻፲፫ን ተመልከቱ)።
4. አዳም-አንዳይ-አማን ጌታ ይህን በምዙሪ የሚገኘውን ቦታ ወደ ፊት ኢየሱስ ከአዳም እና ከጻድቅ ትውልዱ ጋር ለመገናኘት በሚመጣበት ጊዜ የሚሰበሰቡበት ታላቅ መሰብሰቢያ ቦታ እንደሆነ ጠቆመ (ት. እና ቃ. ፫፯፡ ፲፭፡ ፻፯፡ ፻፲–፻፯፡ ፻፲፯ን ተመልከቱ)።
5. ልብርቲ እስር ቤት ጆሴፍ ስሚዝ እና ሌሎች በእዚህ ቦታ ከታህሳስ ቀን ፲፰፻፴፭ እስከ ሚያዝያ ቀን ፲፰፻፴፱ (እ.አ.አ.) ድረስ በማይገባ ሁኔታ ታስረው ነበር። በቤተክርስቲያኗ አስቸጋሪ ጊዜ መካከል፣ ጆሴፍ ጌታን መመሪያ እንዲሰጠው ጠራ እናም ት. እና ቃ. ፻፭–፻፳፫ን ተቀበለ።
6. ናሹ በምዙሪ ወንዝ አጠገብ ተገኝቶ፡ ይህ ቦታ ከ፲፰፻፴፱ እስከ ፲፰፻፴፯ (እ.አ.አ.) ድረስ የቅዱሳን መሰብሰቢያ ቦታ ነበር። በእዚህም ቦታ ቤተመቅደስ ተገነባ፣ እናም እንደ ሙታን ጥምቀት፣ የመንፈስ ስጦታ፣ እና ባልና ሚስቶችን የማስተሳሰር አይነት ስርዓቶች ተጀመሩ። በእዚህም ቦታ የሴቶች መረዳጃ ማህበር በ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.) ተደራጀ። የተቀበሉት ራዕዮችም በተጨማሪ ት. እና ቃ. ፻፳፱–፻፳፱ን ነበሩ።
7. ካርቴጅ በሰኔ ፳፯፡ ፲፰፻፴፬ (እ.አ.አ.) ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ እና ወንድሙ ሀይረም በእዚህ ቦታ ሰማዕት ሆኑ (ት. እና ቃ. ፻፴፭ን ተመልከቱ)።
8. ዊንተር ኮርተርስ ወደ ሶልት ሌክ ሸለቆ በሚጓዙበት የቅዱሳን ለጊዜ የሚሰፍሩበት ቦታ (፲፰፻፴፯–፲፰፻፴፰)። ወደ ምዕራብ ለመጓዝ የእስራኤል ሰፈር ተመስርቶ ነበር (ት. እና ቃ. ፻፴፯ን ተመልከቱ)።
9. ካውንስል ብላፍስ (ኬንስቪል) በታህሳስ ፳፯፡ ፲፰፻፴፯ (እ.አ.አ.) ብሪገም ያንግ ፕሬዘደንት ሆነው፡ የቀዳሚ አመራር በእዚህ ቦታ ተደግፈው ነበር።

6. የቤተክርስቲያኗ ወደ ምዕራብ ጉዞ



1. **ፈየት** በጥር ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.) ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ ከፈየት ወደ ከርትላንድ ኦሀዮ ሄደ። እንዲሰበሰቡ ጌታ ባዘዘው መሰረት የኒው ዮርክ ሶስቱ ቅርንጫፎች (ፈየት፣ ኮልስቪል፣ እና ማንቸስተር) ከሚያዝያ እስከ ግንቦት ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.) ድረስ እርሱን ተከተሉ (ት. እና ቃ. ፴፯–፴፰ን ተመልከቱ)።
2. **ከርትላንድ** ከ፲፰፻፴፩ እስከ ፲፰፻፴፰ (እ.አ.አ.) ድረስ ዋናው የቤተክርስቲያኗ ጠቅላይ መምሪያ በከርትላንድ ውስጥ ነበር።
3. **ኢንዲፔንደንስ** ጌታ ኢንዲፔንደንስን (ጃክሰን ክፍለ አገር ምዙሪ) እንደ ፅዮን ዋና ቦታ በሐምሌ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.) ጠቆማት (ት. እና ቃ. ፶፯፥፫ን ተመልከቱ)። በአመፅ የተነሱ ሰዎች ቅዱሳንን ከጃክሰን ክፍለ አገር በህዳር ፲፰፻፴፫ (እ.አ.አ.) በግድ አስወጧቸው።
4. **ልብርቲ** የጃክሰን ክፍለ አገር ቅዱሳን ከ፲፰፻፴፫ (እ.አ.አ.) ቅዱስን እንደገና እንዲወጡ እስከተደረገበት እስከ ፲፰፻፴፮ (እ.አ.አ.) ድረስ በክሌይ ክፍለ አገር ተሰበሰቡ። ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ እና ከአምስት ሌሎች ጋር በማይገባ ሁኔታ ከታህሳስ ፲፰፻፴፰ እስከ ሚያዝያ ፲፰፻፴፱ (እ.አ.አ.) ድረስ በእዚህ ቦታ ታሰሩ።
5. **ፋር ዌስት** ከ፲፰፻፴፮–፲፰፻፴፰ (እ.አ.አ.) ድረስ በእዚህ ቦታ መሸሸጊያ ተመስርቶ ነበር። በ፲፰፻፴፰ (እ.አ.አ.) የቤተክርስቲያኗ ጠቅላይ መምሪያ ነበር። በ፲፰፻፴፰–፲፰፻፴፱ (እ.አ.አ.) ቅዱሳን ከኢሊኖይ እንዲሸሹ ተገደዱ።
6. **ናቩ** ከ፲፰፻፴፱–፲፰፻፵፮ (እ.አ.አ.) ድረስ የቤተክርስቲያኗ ጠቅላይ መምሪያ ነበር። ከነቢዩ እና ከወንድሙ ሀይረም ሰማዕት በኋላ፣ ቅዱሳን ወደ ምዕራብ ሄዱ።
7. **ካውንስል ብላፍስ** ፈር ቀዳጆች በሰኔ ፲፰፻፵፮ (እ.አ.አ.) በእዚህ ቦታ ላይ ደረሱ። የሞርሞን የሻለቃ ጦር አባላት በሐምሌ ፳፩፣ ፲፰፻፵፮ (እ.አ.አ.)፣ በጄምስ አለን አመራር ስር ከእዚህ ቦታ ሄዱ።
8. **ዊንተር ኮርተርስ** ከ፲፰፻፵፮–፲፰፻፵፰ (እ.አ.አ.) ድረስ ጊዜአዊ መስፈሪያ የሆነ ቦታ ነበር። የመጀመሪያው ቡድን በፕሬዘደንት ብሪገም ያንግ አመራር ስር ወደ ምዕራብ በሚያዝያ ፲፰፻፵፯ (እ.አ.አ.) መሄድ ጀመሩ።
9. **ፎርት ሌቨንዎርዝ** የሞርሞን የሻለቃ ጦር በነሀሴ ፲፰፻፵፮ (እ.አ.አ.) ወደ ምዕራብ ጉዞአቸውን ከመጀመራቸው በፊት በእዚህ ቦታ ታጥቀው ነበር።
10. **ሳንታ ፌ** በጥቅምት ፲፱፣ ፲፰፻፵፮ (እ.አ.አ.) የሞርሞን የሻለቃ ጦርን ከእዚህ ሲጓዙ ፊሊፕ ኮክ ይመራቸው ነበር።
11. **ፑዌብሎ** ሶስት የታመሙ የተገነጠሉ የሞርሞን የሻለቃ ጦር አባላት እስከሚሻላቸው ድረስ ወደ ፑዌብሎ እንዲሄዱ ታዝዘው ነበር፣ በእዚህ፣ ከ፲፰፻፵፮–፲፰፻፵፯ (እ.አ.አ.) ድረስ ከምስስፒ ከመጡት ቅዱሳን ጋር ቆዩ። እነዚህ ቡድኖች ወደ ሶልት ሌክ ሸለቆ በሐምሌ ፲፰፻፵፯ (እ.አ.አ.) ገቡ።
12. **ሳን ዲያጎ** የሞርሞን የሻለቃ ጦር ወደ እዚህ ቦታ ያደረጉትን የ፫ ሺህ ፪፻ ኪሎ ሜትር ጉዞአቸውን በጥር ፳፱፣ ፲፰፻፵፯ (እ.አ.አ.) ፈጸሙ።
13. **ሎስ አንጀለስ** የሞርሞን የሻለቃ ጦር በእዚህ ቦታ ላይ በሐምሌ ፲፮፣ ፲፰፻፵፯ (እ.አ.አ.) ተለቀቁ።
14. **ሳክርመንቶ** አንዳንድ የተለቀቁ የሻለቃ ጦር አባላት በእዚህ ቦታ ላይ እና በአሜሪካ ወንዝ ላይ በስተምስራቅ ባለው በሳተር ሚል ውስጥ ሰሩ። በጥር ፲፰፻፵፰ (እ.አ.አ.) ወርቅ በተገኘበት ግዜ በእዚያ ይገኙ ነበር።
15. **ሶልት ሌክ ስቲ** ከ፲፰፻፵፯ (እ.አ.አ.) እስከ አሁን ድረስ የቤተክርስቲያኗ ተቅላይ መምሪያ። ብሪገም ያንግ በሶልት ሌክ ሸለቆ ውስጥ በሐምሌ ፳፬፣ ፲፰፻፵፯ (እ.አ.አ.) ደረሱ።

7. የአለም ካርታ

ሀ
ለ
ሐ
መ
ሠ
ረ
ሰ
ሸ
ቀ
በ
ተ
ቸ
ኀ
1
2
3
4
የሰሜን ፓስፊክ ውቅያኖስ
ኦሽያኒያ
ኦሙስትሬሊያ
ኤስያ
የኢንድያን ውቅያኖስ
ኦሮፓ
አፍሪካ
አንታርክቲካ
የሰሜን አትላንቲክ ውቅያኖስ
የደቡብ አትላንቲክ ውቅያኖስ
ደቡብ አሜሪካ
መካከለኛው አሜሪካ
የሰሜን አሜሪካ
ፓስፊክ ውቅያኖስ
የደቡብ ፓስፊክ ውቅያኖስ
የሰሜን ፓስፊክ ውቅያኖስ

የቤተክርስቲያኗ ታሪክ ካርታዎች ዝርዝር

የካርታዎች ዝርዝር በካርታዎች ላይ አንድ ቦታን ለማግኘት ይረዳችኋል። እያንዳንዱ ቦታ የካርታ ቁጥር እና መጠቆሚያ በቁጥር እና በፊደል የተሰራ ነው። ለምሳሌ የፎርት ሆል ማመልከቻ እንደ 6:ለ1 ተሰጥቷል፣ ይህም ካርታ 6፣ አራት መአዘን ለ1 ማለት ነው። በእያንዳንዱ ካርታ ላይ ያለ አራት መአዘንን ለማግኘት በካርታው ከፍተኛ እና በጎን ላይ የሚገኙትን ማጣቀሻዎች ተጠቀሙባቸው። የቦታዎቹ ሌላ ስም በቅንፎች ውስጥ ተዘርዝረዋል፣ ለምሳሌ፣ ካውንስል ብላፍስ (ኬንስቪል)።

ሀርስ፣ ማርቲን፣ የእርሻ ቦታ፣ ፓልማይራ አካባቢ, 2:ለ1
ሀይረም፣ ኦሀዮ, 3:መ4
ሀድሰን ወንዝ፣ ኒው ዮርክ, 1:ሐ3
ሁሮን ሀይቅ, 3:ሐ1
ሃርመኒ፣ ፔንስልቬኒያ, 1:ለ3, 3:ሸ3
ሃትዌይ ብሩክ፣ ፓልማይራ አካባቢ, 2:ለ2, 2:መ4
[የ]ሃኑ የመፍጨያ ቤት፣ ምዙሪ, 5:መ3
[የ]ሀይረም ስሚዝ ቤት፣ ከርትላንድ, 4:ለ4
[የ]ሀንድ ባህር, 7:ረ3
[የ]ሀንዶች አገር, 5:ለ2, 6:መ1, 6:መ3

ለበኖን፣ ኒው ሀምሻየር, 1:መ2
ልብርቲ፣ ምዚሪ, 5:መ4, 6:ሠ2
ሎስ አንጀለዝ, 6:ሀ3

መሀከለኛው አሜሪካ, 7:ለ2
መቸዶን ታውንሽፕ፣ የፓልማይራ አካባቢ, 2:ሀ1
[የ]መክኢልውን መጠ ማዘጋ፣ ምዙሪ, 5:ሠ4
ሚሽን ሳን ሉዊስ ሬይ, 6:ለ4
ሚዶን፣ ኒው ዮርክ, 3:ረ2
ማሳቹሴት, 1:ሐ3
ማርኬል ሮድ፣ ከርትላንድ, 4:ሀ2
ማንችስተር ታውንሽፕ፣ ኒው ዮርክ, 1:ሀ3, 2:መ3, 3:ሰ2
ማውንት ፒስጋ፣ አየዋ, 5:መ1
ሜክሲኮ, 6:ለ3
ሜይን, 1:መ1
ምስስፒ ወንዝ, 5:ሰ3
ምዙሪ, 5:ረ3, 6:ሠ3
ምዙሪ ወንዝ, 5:ሐ2, 5:ረ4
ሞንትሮስ፣ አየዋ, 5:ረ2

ረድ ክሪክ፣ ፓልማይራ አካባቢ, 2:መ2
ሪትስ ሚል፣ ከርትላንድ, 4:ለ2
ራመስ፣ ኢለኖይ, 5:ሰ2
ርችመንድ፣ ምዙሪ, 5:መ4
ሪዮ ግራንድ, 6:ሐ4
ሮድ አይላንት, 1:መ3
ሯቸስተር፣ ኒው ዮርክ, 3:ረ1

ሰመተሪ፣ ከርትላንድ, 4:ለ3
ሰሜን አሜሪካ, 7:ለ2
[የ]ሰሜን አትላንቲክ ውቅያኖስ, 7:ሐ2
[የ]ሰሜን ፓስፊክ ውቅያኖስ, 7:ሀ2, 7:ሸ2
[የ]ሰሜን ፕላተር ወንዝ, 6:ሐ1
ሰስኮሀና ወንዝ፣ ፔንስ ልቬኒያ, 1:ሀ4, 3:ሰ3
ሳን በርናርዲኖ, 6:ለ3
ሳን ዲያጎ, 6:ለ4
ሳን ፍራንሲስኮ, 6:ሀ2
ሳንታ ፌ, 6:ሐ3
ሳክርመንቶ, 6:ሀ2
ሴለም፣ ማሳቹሴት, 1:መ3
ሴይንት ሉዊስ፣ ምዙሪ, 5:ሸ4
ስታፈርድ ሮድ፣ ፓልማይራ አካባቢ, 2:ለ4
ስቶኒ ብሩክ፣ ከርትላንድ, 4:ሐ3
ስኔክ ወንዝ, 6:ለ1
ስፕሪንግፊልድ፣ ኢለኖይ, 5:ሸ2
ሶልት ሌክ ስቲ, 6:ለ2
[የ]ስድኒ ሪግደን ቤት፣ ከርትላንድ, 4:ለ4
ሷሚል፣ ከርትላንድ, 4:ለ3
ሼረን፣ ቨርሞንት, 1:ሐ2
ሾል ክሪክ፣ ምዙሪ, 5:መ3

ቅዱስ ዋሻ፣ ፓልማይራ አካባቢ, 2:ለ3

ባንክ፣ ከርትላንድ, 4:ለ4
ባፈሎ፣ ኒው ዮርክ, 3:ሠ2
ቦስተን፣ ማሳቹሴት, 1:መ3

ተንብሪጅ፣ ቨርሞንት, 1:ሐ2
ቱሳን, 6:ለ4
ታነሪ፣ ከርትላንድ, 4:ለ2
ትምህርት ቤት፣ ከርትላንድ, 4:ለ3
ቶምሰን፣ ኦሀዮ, 3:መ3
ቶሯንቶ፣ ካነዳ, 3:ሠ1
ቶፕስፊልድ፣ ማሳቹሴት, 1:መ3
ቻሪተን ወንዝ፣ ምዙሪ, 5:ሠ2
ቻግሪን ወንዝ፣ የምስራቅ ቅርንጫፍ፣ ከርትላንድ, 4:ለ1
ችሊኮት መንገድ፣ ከርትላንድ, 4:ለ4

ኒው ሀምሸር, 1:መ2
[የ]ኒውል ኬ ውትኒ ሱቅ፣ ከርትላንድ, 4:ለ2
[የ]ኒውል ኬ ውትኒ ቤት፣ ከርትላንድ, 4:ለ2
ኒው ዮርክ, 1:ለ3, 3:ሠ3, 6:ሰ1
ኒው ዮርክ ስቲ, 1:ሐ4, 6:ሰ1
ኒው ጀርዚ, 1:ለ4

ናቩ ኢለኖይ, 5:ረ1, 6:ሠ2
ኖርውች፣ ቨርሞንት, 1:መ2

አልበኒ፣ ኒው ዮርክ, 1:ሐ2
[የ]አልቭን ስሚዝ መቃብር ቦታ፣ ፓልማይራ, 2:ሐ2
አምኸርስት፣ ኦሀዮ, 3:ሐ4
አርሚንቶን ስኩልሀውስ መንገድ፣ ፓልማይራ አካባቢ, 2:መ3
አርካንሳስ ወንዝ, 6:መ3
አሸሪ፣ ከርትላንድ, 4:ለ3
አትላንቲክ ባህር, 1:መ4, 6:ሸ2
አንታርቲካ, 7:ሠ4
አውስትራሊያ, 7:ሰ3
አውሮፓ, 7:ሠ1
አየዋ, 5:ሠ1, 6:ሠ2
[የ]አይዛክ ሞርሊ የእርሻ ቦታ፣ ከርትላንድ, 4:መ1
አዳም-ኦንዳይ-አማን፣ ምዙሪ, 5:መ3
አፍሪቃ, 7:ሠ2
ኢለኖይ, 5:ሸ3, 6:ረ2
[የ]ኢሪ ሀይቅ, 3:መ3
ኢንዲፔንደንስ፣ ምዙሪ, 5:መ4, 6:ሠ2
ኢንድያና, 6:ረ2
[የ]እሪ መስኖ፣ ኒው ዮርክ, 2:ሀ2, 3:ረ1
እስያ, 7:ረ2
[የ]እትመት ቢሮ፣ ከርትላንድ, 4:ለ4
ኦሀዮ, 3:ለ4, 6:ረ2
ኦሬንጀ ግዛት, 6:ሀ1

ኦሬንጅ፣ ኦሀዮ, 3:ሐ4
ኦንታሪዮ ሀይቅ, 1:ሀ2, 3:ረ1
ኦንታሪዮ የግዛት ክፍል፣ ኒው ዮርክ, 2:ሀ3, 2:መ3

[የ]ከሞራ ኮረብታ፣ ፓልማይራ አካባቢ, 2:ሐ4
ከርትላንድ፣ ኦሀዮ, 3:ሐ3, 6:ረ1
[የ]ከርትላንድ ቤተመቅደስ, 4:ለ4
ከነትከት, 1:ሐ3
[የ]ከነትከት ወንዝ, 1:መ1
ካሊፎርንያ, 6:ሀ3
[የ]ካሊፎርንያ መንገድ, 6:ለ2
ካርቴጅ፣ ኢለኖይ, 5:ሰ2
ካናዳ, 1:ሐ1, 3:ሐ3, 6:ረ1
[የ]ካናዳ ወንዝ, 6:መ3
ካናዳጉዋ መንገድ፣ ፓልማይራ አካባቢ, 2:ሐ3
ካውንስል ብላፍስ (ኬንስቪል)፣ ኦሀዮ, 5:ሐ1, 6:ሠ2
ካውደሪ መንገድ፣ ከርትላንድ, 4:ሀ3
ክሊቭላንድ፣ ኦሀዮ, 3:ሐ4
ክውንሲ፣ ኢለኖይ, 5:ሰ2, 6:ሠ2
ኮልስሊቭ፣ ኒው ዮርክ, 1:ለ3, 3:ሸ3
ዋሽንግተን፣ ዲ.ሲ., 6:ሰ2
ዌይን የግዛት ክፍል፣ ኒው ዮርክ, 2:ሀ3, 2:መ3
ውቲንግሀም፣ ቨርሞንት, 1:ሐ3
ውትኒ መንገድ፣ ከርትላንድ, 4:ሀ3
ውንተር ኮርተርስ፣ የህንድ ግዛት, 5:ለ1, 6:ሠ2

ደቡብ ብሬንብርጅ፣ ኒው ዮርክ, 1:ለ3, 3:ሸ3
ደቡብ አሜሪካ, 7:ሐ3
[የ]ደቡብ አትላንቲክ ውቅያኖስ, 7:መ3
ደቡብ ፓስፊክ ውቅያኖስ, 7:ሀ3
ደቡብ ፕላት ወንዝ, 6:ሐ2
ዴለዌር ወንዝ, 1:ለ4
ድዊት፣ ምዙሪ, 5:ሠ4

ጃክሰን ካውንቲ፣ ምዙሪ, 5:መ4
[የ]ጆሴፍ ስሚዝ ቀዳማዊ በፍልጥ እንጨት የተሰራ ቤት፣ ፓልማይራ አካባቢ, 2:ለ3
[የ]ጆሴፍ ስሚዝ ቀዳማዊ ቤት, 2:ለ3
[የ]ጆሴፍ ስሚዝ ቀዳማዊ የእርሻ ቦታ፣ ፓልማይራ አካባቢ, 2:ለ3
[የ]ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ ቤት, 3:ሸ3, 4:ለ3
[የ]ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ የተለያዩ እቃዎች የሚሸጥበት ሱቅ፣ ከርትላንድ, 4:ለ3
ጆሴፍ ስትሪት፣ ከርትላንድ, 4:ሀ4
[የ]ጆሴፍ ናይት ታላቁ ቤት፣ ኮልስቪል ታውንሽፕ፣ ኒው ዮርክ, 3:ሸ3
ጆንሰን፣ ሆቴል፣ ከርትላንድ, 4:ለ2

ጊላ ወንዝ, 6:ለ4
ጊልሱም፣ ኒው ሀምሸር, 1:መ2
ጋላቲን፣ ምዙሪ, 5:መ3
ጋርደን ግሮቭ፣ አየዋ, 5:መ1
ግራንዲን፣ ኢ. ቢ.፣ የማተሚያ ቤት፣ ፓልማይራ, 2:መ2
ግራንድ ሪቨር፣ ምስስፒ, 5:ሐ2
ግሬት ሶልት ሌክ, 6:ለ2

[የ]ጥምቀት ቦታ፣ ከርትላንድ, 4:ለ2

ፊንገር ሀይቅ፣ ኒው ዮርክ, 1:ሀ3, 3:ሰ2
ፋርሚንግተን ከተማ፣ ፓልማይራ አካባቢ, 2:ሀ4
ፋር ዌስት፣ ምዙሪ, 5:መ3, 6:ሠ2
ፊየት፣ ኒው ዮርክ, 1:ሀ3, 3:ሰ2, 6:ሰ1
ፍለደልፊያ፣ ፔንስልቬንያ, 1:ለ4, 6:ሰ2
ፍሪደም፣ ኒው ዮርክ, 3:ረ2
ፍሽንግ ወንዝ፣ ምዙሪ, 5:መ3
ፍክስ ሮድ፣ ፓልማይራ አካባቢ, 2:ሀ3
ፎርት ሆል, 6:ለ1
ፎርት ለቭንወርዝ, 5:መ4, 6:ሠ2
ፎርት ላረሚ, 6:ሐ2
ፎርት ብሪጀር, 6:ሐ2

ፑዌብሎ, 6:ሐ3
ፒኮስ ወንዝ, 6:ሐ4
ፓልማይራ መንደር፣ ኒው ዮርክ, 2:ሐ2
ፓልማይራ ታውንሽፕ፣ ኒው ዮርክ, 1:ሀ3, 2:መ1, 3:ሰ2
ፓስፊክ ውቅያኖስ, 6:ሀ1, 7:ለ3
ፕሪስበርግ፣ ኒው ዮርክ, 3:ሠ2
ፔንስልቬንያ, 1:ሀ4, 3:ረ4, 6:ሰ1
ፕላት ወንዝ, 5:ለ1

ቨርሞንት, 1:ሐ2

የቤተክርስቲያኗ ታሪክ ፎቶዎች

እነዚህ አስፈላጊ የቤተክርስቲያኗ ታሪክ ቦታዎች ፎቶዎች የመጀመሪያው የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የተራመዱባቸው፣ የዚህ ዘመን ነቢያት የኖሩበትና ያስተማሩባቸው፣ እናም ብዙ የቅዱሳት መጻህፍት ድርጊቶች የተፈጸሙባቸው ምድሮችን ያሳያሉ።

ማጠቃለያ

ከዚህ በታች የሚገኘው ካርታ በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉ ፎቶዎች የት እንደሚገኙ ያሳያሉ። በሚቀጥሉት ገጾች ላይ፣ እያንዳንዱ ፎቶ ስለድርጊቱ አጭር መግለጫ አለው። በተጨማሪ የት ለማንበብ እንደምትችሉ እንድታውቁ፣ ከቅዱሳን መጻህፍት ጥቅሶች ጋር በእዚያ አካባቢ የሚገኙትን ታላቅ የቅዱሳት መጻህፍት ድርጊቶችን ይዘረዝራሉ።

1. ቅዱስ ጥሻ
2. ከሞራ ኮረብታ እና ማንቸስተር-ፓልማይራ አካባቢ
3. በፍልጥ እንጨት የተሰራ የጆሴፍ ስሚዝ ቀዳማዊ ቤት
4. ግራንዲን የማተሚያ ሱቅ
5. ሰስኮሀና ወንዝ
6. የፒተር ዊትመር ቀዳማዊ ቤት
7. የኒውል ኬ ዊትኒ እና ተዋንያን ሱቅ
8. የጆን ጆንሰን ቤት
9. የከርትላንድ ቤተመቅደስ
10. አዳም-ኦንዳይ-አማን
11. የፋር ዌስት የቤተመቅደስ መገንቢያ ቦታ
12. ልብርቲ እስር ቤት
13. የናቩ አዳራሽ ቤት
14. የነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ የቀይ ሸክላ ሱቅ
15. የናቩ ቤተመቅደስ
16. የካርቴጅ እስር ቤት
17. ወደ ምዕራብ መሰደድ
18. የሶልት ሌክ ቤተመቅደስ



1. ቅዱስ ጥሻ

ቅዱስ ጥሻው የሚገኘው በፓልማይራ እና በማንቸስተር ከተማዎች፣ በኒው ዮርክ ውስጥ ነው። ይህ ጥሻ በ፲፰፻፳፭ (እ.አ.አ.) የስሚዝ ቤተሰብ በፍልጥ እንጨት የተሰራው ቤት ከነበርበት በስተምዕራብ በኩል ነበር።

ታላቅ ድርጊቶች፥ እግዚአሔር አብ እና ልጁ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የታዩት በዚህ ጥሻ ውስጥ ነበር (ጆ.ስ.—ታ. ፩፣ ፲፱–፳)።

2. ከሞራ ኮረብታ እና ማንቸስተር-ፓልማይራ አካባቢ

ወደ ሰሜን ሲመለከቱ፣ ይህ ፎቶ በማንቸስተር፣ ኒው ዮርክ ውስጥ ያለውን የከሞራ ኮረብታ ያሳያል። ኮረብታው በፎቶው ከቀኝ ማዕዘን እስከ ፎቶው መካከል ግማሽ ድረስ እንደሆነ ይታያል። በኮረብታው በስተሰሜን በኩል ያለው ሀውልት መልአኩ ሞሮኒን እና የመፅሐፈ ሞርሞን መም ጣትን የሚያከብር ነው። የከሞራ ኮረብታ ከቅዱስ ጥሻው ፤ኪሎ ሜትር ወደ ደቡብ ምስራቅ ያለ ነው። በፎቶው ላይ ከፍ ብሎ የሚታየውም ፓልማይራ ነው፣ ይህም ፤ ተኩል ኪሎ ሜትር የሚርቅ ነው። የስሚዝ የእርሻ ቦታ እና ቅዱስ ጥሻው የሚገኙት በፎቶው በከፍተኛው በስ ተግራ በኩል ነው።

ታላቅ ድርጊቶች፥ የጆሴፍ ስሚዝ ቤተሰብ በመጀመ ሪያው ራዕይ ጊዜ በዚህ ቦታ ይኖሩ ነበር (ጆ.ስ.—ታ. ፤፡፣ ፫)። በ፵፯፤ ዓ.ም.፣ ሞሮኒ በከሞራ ኮረብታ የህዝ ቡን ቅዱስ ታሪክ የያዙትን የወርቅ ሰሌዳዎችን ቀበረ (ቃላት ፤፡–፤፫፣ ሞር. ፤፡፡–፤፣ ሞሮኒ ፤፡–፤–፪)። ይህም ሞሮኒ ሰሌዳዎችን የት እንደሚያገኛቸው ለጆሴፍ። ሞሮኒ እነዚህን ለእርሱ በ፤፯፤፤፯ (እ.አ.አ.) አሳልፎ አስረከበ (ት. እና ቃ. ፳፯፡፡፣ ፤፤፳፯፡፡፣ ጆ.ስ.—ታ. ፤፡፣ ፴፫–፴፭፣ ፶፤–፶፪፣ ፶፶)።

3. በፍልጥ እንጨት የተሰራ የጆሴፍ ስሚዝ ቀዳማዊ ቤት



በፓልማይራ፣ ኒው ዮርክ ውስጥ የፍልጥ እንጨት ቤት በመጀመሪያ ተገንብቶበት በነበረው ቦታ ላይ በአምሳያ ነት የተሰራ የጆሴፍ ስሚዝ ቀዳማዊ ቤት። የመጀመሪያ ውን የስሚዝ ቤተሰብ ፤ ተኩል ቤት የሚሆን ከፍልጥ እን ጨት ቤት የተሰራው ወደ ፓልማይራ ከገቡ ከአጭር ጊዜ በኋላ ነበር። ቤተሰብ ከ፲፰፻፲፱ እስከ ፲፰፻፳፭ (እ.አ.አ.) ድረስ በዚህ ይኖሩ ነበር።

ታላቅ ድርጊቶች፥ ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የትኛው ቤተክርስ ቲያን ትክክለኛ እንደሆነ ለማወቅ በሚታገልበት ጊዜ በዚህ ቤት ውስጥ መፅሐፍ ቅዱስን ያጠና ነበር (ጆ.ስ.—ታ. ፤ ፲፭–፲፰)። ሞሮኒ በጆሴፍ ስሚዝ ታየ እናም ስለመፅ ሐፈ ሞርሞን ሰሌዳዎች ነገርው (ጆ.ስ.—ታ. ፤ ፴–፴፯)።

4. ግራንዲን የማተሚያ ሱቅ

በ፲፰፻፴ (እ.አ.አ.) የመጀመሪያው የመፅሐፈ ሞርሞን ቅጂ የታተመበት በፓልማይራ፣ ኒው ዮርክ የሚገኘው እንደ ገና የተገነባው የኤግበርት ቢ ግራንዲን የማተሚያ ሱቅ። የመፅሐፈ ሞርሞን ፲ ሺህ መፅሐፎች የሚታተሙበትን ገንዘብ ለመክፈል ማርቲን ሀሪስ የእርሻ ቦታውን በብ ድር አስያዘ እናም አንድ ክፍሉንም ሸጠ። ለማተም ዝግ ጅቱ የተጀመረው በነሐሴ ፲፰፻፴፬ (እ.አ.አ.) ነበር፣ እናም ታትመው የተፈጸሙት መፅሀፎች ይገኙ የነበሩትም በመ ጋቢት ፳፮፣ ፲፰፻፴ (እ.አ.አ.) ነበር።

ታላቅ ድርጊቶች፥ ማርቲን ሀሪስ የመፅሐፈ ሞርሞን ማተ ሚያ እዳን ለመክፈል ንብረቱን በፈቃደኝነት እንዲሰጥ ታዝዞ ነበር (ት. እና ቃ. ፲፱፥ ፳፮–፴፭)።

5. ሰስኮሀና ወንዝ

ይህ ፎቶ በሀርመኒ ከተማ፣ ፔንስልቬኒያ ውስጥ ያለውን የሰስኮሀና ወንዝ ያሳያል።

ታሳቅ ድርጊቶች፥ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ ወደ ሀርመኒ ለመጀመሪያ ጊዜ በ፲፰፻፳፭ (እ.አ.አ.) የመጣው ስራ ለማ ግኘት ነበር። እርሱ እና አባቱ በዚህ አጠገብ፣ ከወደፊት ባለቤቱ ኤማ ሄል በተገናኘበት በአይዛክ ሄል ቤት ውስጥ በመክፈል ይኖሩ ነበር (ጆ.ስ.—ታ. ፩፥ ፶፯–፶፯)። ጆሴፍ እና ኤማ በጥር ፲፰፣ ፲፰፻፳፭ (እ.አ.አ.) ተጋቡ። ነቢዩ በማንቸስተር፣ ኒው ዮርክ ውስጥ በመስከረም ፳፪ ቀን ፲፰፻፳፭ (እ.አ.አ.) የወርቅ ሰሌዳዎችን ተቀበለ፣ እናም ወዲያውም ከኤማ ጋር ወደ ሀርመኒ ሄዶ ሰሌዳዎችን መተ ርጎም ጀመረ። መፅሐፈ ሞርሞን በሚተረጉምበት ጊዜ፣ ጆሴፍ እና ኦሊቨር ካውደሪ ስለጥምቀት ተጨማሪ ነገሮ ችን ለማወቅ ፈለጉ እናም ስለእዚህ ርዕስ ለማወቅ ወደ ጌታ ለመጸለይ በዚህ አጠገብ ወደነበረ ጫካ ሄዱ። ለዚህ ጸሎ ትም መልስ፣ በግንቦት ፲፭፣ ፲፰፻፳፱ (እ.አ.አ.) መጥምቁ ዮሐንስን አዩ (ጆ.ስ.—ታ. ፩፥ ፷፯–፷፱፤ ት. እና ቃ. ፲፫)። እርሱም ጆሴፍን እና ኦሊቨርን በአሮናዊ የክህነት ስልጣን ሾማቸው። ከእዚያም ወደ ወንዙ ገቡ እናም እርስ በርስ ለጋጢያት ስርየት በመነከር ተጠመቁ። ጆሴፍ እና ኦሊ ቨር ከእዚያም በጓላ እርስ በራስ በአሮናዊ የክህነት ስል ጣን እንዲሾሙ መመሪያ ሰጣቸው። ከእዚህ ትንሽ ጊዜ በኋላ፣ ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ፣ እና ዮሐንስ በሀርመኒ እና በኮ ልስቪል መካከል ታይተው ጆሴፍን እና ኦሊቨርን በመልክ ጴጴቅ የክህነትሹመት ሰጧቸው (ት. እና ቃ. ፳፯፥ ፲፪–፲፫፣ ፻፳፰፥ ፳)።

6. የፒተር ዊትመር ቀዳማዊ ቤት



ይህ የፍልዋ እንጨት ቤት የፒተር ዊትመር ቀዳማዊን የመጀመሪያ ቤት የሚመስል ነው።

ታላቅ ድርጊቶች፥ ጆሴፍ ስሚዝ በእዚህ ቦታ የመፅሐፈ ሞርሞን ትርጉም ስራውን በሰኔ ፲፰፤፰፳፱ (እ.አ.አ.) ፈጸመ። በዚህ ቤት አጠገብ ባለው ጫካ ውስጥ፣ ሶስቱ ምስክሮች መልአክ ሞሮኒን እና የወርቅ ሰሌዳዎችን ተመለከቱ። ምስክራቸውም በሚታተሙት የመፅሐፈ ሞርሞን መፅሐፎች ውስጥ በሙሉ ታትመዋል። በሚያዝያ ፮፣ ፲፰፤፰፴ (እ.አ.አ.)፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን ህጋዊ መደራጀትን ለመመልከቱ ፰ የሚሆኑ ሰዎች በፒተር ዊትመር ቤት ውስጥ ተሰበሰቡ (ት. እና ቃ. ፳)። በትምህርት እና ቃል ኪዳኖች ውስጥ የሚገኙት ሀያ ራዕዮች የተቀበሉት በየፒተር ዊትመር ቤት ውስጥ ነበር።

7. የኒውል ኬ ዊትኒ እና ተዋንያን ሱቅ



የኒውል ኬ ዊትኒ የንግድ ቤት በከርትላንድ ውስጥ በደረሱት የቤተክርስቲያኗ ታሪክ ውስጥ ታላቅ ክፍል ነበረው። ጆሴፍ እና ኤማ በዚህ ቦታ ለአጭር ጊዜ ኖሩ። ብዙ ዋና ራዕዮችም በእዚህ ቦታ ተቀብለው ነበር። ከጥር ፲፰፻፣ ፲፰፻፴፫ እስከ ሚያዝያ ፲፰፻፴፫ (እ.አ.አ.) አካባቢ ድረስ የነቢያት ትምህርት ቤትም እዚህ ቦታ ውስጥ ነበር። ታላቅ ድርጊቶች፥ ነቢዩ ጆሴፍ የጥበብ ቃል (ት. እና ቃ. ፹፱) ራዕይን ተቀበለ። የመፅሐፍ ቅዱስ የጆሴፍ ስሚዝ ትርጉም (ጆ. ስ. ት) አብዛኛው ስራውን የፈጸመው በእዚህ ቦታ ነበር።

8. የጆን ጆንሰን ቤት

የጆን እና የአሊስ ጆንሰን ቤት የነበረው በሀይረም፣ ኦሀዮ ውስጥ ነበር። ይህም ክፍል በሁለተኛው ደረጃ ላይ የሚገኝ ነበር።

ታላቅ ድርጊቶች፥ ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ እና ባለቤቱ ኤማ በእዚህ ቤት ውስጥ ይኖሩ ነበር። ጆሴፍ እና ስድኒ ሪግ ደን በየካቲት ፤፲፯፣ ፤፲፰፻፴፪ (እ.አ.አ.) የክብር ደረጃዎችን አስደናቂ ራዕይ ሌሎች ተሰብስበው በተገኙበት ተቀበሉ (ት. እና ቃ. ፹፯)። ነቢዩ ጆሴፍ ደግሞም በመፅሐፍ ቅዱስ የጆሴፍ ስሚዝ ትርጉም (ጆስት) ላይ በዚህ ቤት ውስጥ ይሰራ ነበር። በመጋቢት ፳፬ ቀን ፤፲፰፻፴፪ (እ.አ.አ.) ምሽት፣ ጆሴፍ እና ኤማ በእዚህ እየኖሩ እያሉ፣ በአመጽ የተነሳሱ ከሀጂዎች እና ጸረ-ሞርሞኖች ጆሴፍንና ስድኒን ደበደቡ እናም በሬንጅ እና በላባ ቀብተው ሸፈኗቸው።

9. የከርትላንድ ቤተመቅደስ



የከርትላንድ ቤተመቅደስ የሚገኘው በከርትላንድ፣ ኦሀዮ ውስጥ ነው።

ታላቅ ድርጊቶች፥ የከርትላንድ ቤተመቅደስ በዚህ ዘመን በመጀመሪያ የተገነባ ቤተመቅደስ ነው (ት. እና ቃ. ፹፰፡፲፱፣ ፻፲፮)። በዚህ ቤተመቅደስ ውስጥ፣ ጆሴፍ የሰለስቲያል መንግስት ራዕይን አየ (ት. እና ቃ. ፻፴፯)። ይህም በመጋቢት ፳፯፣ ፲፰፻፴፯ (እ.አ.አ.) ተቀደሰ (ት. እና ቃ. ፻፴)። በሚያዝያ ፫፣ ፲፰፻፴፯፣ ጌታ ታየ እና ለህዝቡ ቃሉን እንደሚገልጽበት ቦታም ቤተመቅደሱን ተቀበለ (ት. እና ቃ. ፻፲፡፩–፲)። በእዚህ ከታየ በኋላ፣ ጆሴፍ ስሚዝ እና ኦሊቨር ካውደሪ በሙሴ፣ በኤልያ፣ እና በኤልያስ ተጎበኙ፣ ሁሉም አንዳንድ የክህነት ስልጣን ቁልፎችን እና አስፈላጊ መረጃዎችን ሰጧቸው (ት. እና ቃ. ፻፲፡፲፩–፲፮)። በስደት ምክንያት ቅዱሳን ከከርትላንድ በመሸሽ ከመውጣታቸው በፊት ለሁለት አመት ቤተመቅደሱ አገለገላቸው።

10. አዳም-ኦንዳይ-አማን

በጋላቲን ማህብረሰብ አጠገብ፣ በሰሜን ምዙሪ የሚገኝ ውን ጸጥተኛ፣ አስደሳች፣ ሸለቆ፣ ከአዳም-ኦንዳይ-አማን ሸለቆ ወደ ምስራቅ የሚመለከት።

ታላቅ ድርጊቶች፥ ከመሞቱ ሶስት አመት በፊት፣ አዳም ጻድቅ ትውልዱን በዚህ ሸለቆ ውስጥ ሰበሰበ እናም በእነር ሱም ላይ የመጨረሻ በረከቱን ሰጠ (ት. እና ቃ. ᏥᏬ፥ ᏭᏮ–ᏭᏬ)። በᏗᏥᏥᏭᏥ (እ.አ.አ.) አዳም-ኦንዳይ-አማን በᏥᏥ እስከ ᏥᏬ ሺህ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የሰፈሩበት ቦታ ነበር። ቅዱሳን ይህን ስፍራ ከምዙሪ በግድ ሲወጡ ጥለ ውት ሄዱ። ክርስቶስ በግርማ ዳግም ከመምጣቱ በፊት፣ አዳም እና ከዘመናት ሁሉ ቅዱሳን የሆኑትን የሚጨም ሩት ጻድቅ ትውልዱ እንደገና በዚህ ሸለቆ ውስጥ ከአ ዳኝ ጋር ለመገናኘት ይሰበሰባሉ (ዳን. Ᏼ፥ Ᏽ–Ᏻ፣ ᏗᏮ–ᏗᏰ፣ ት. እና ቃ. ᏥᏬ፣ ᏥᏬ፥ ᏭᏮ–ᏭᏬ፣ ᏥᏗᏬ)።

11. የፋር ዌስት የቤተመቅደስ መገንቢያ ቦታ



የፋር ዌስት፣ ምዙሪ ስፍራ በጃክሰን እና ክሌይ ግዛት ውስጥ ለተሰደዱት ለ፲ ሺህ እስከ ፮ ሺህ ቅዱሳን መሸሸጊያ ነበር። በ፲፰፻፴፰ (እ.አ.አ.) ጌታ ቅዱሳን ቤተ መቅደስ በዚህ እንዲገነቡ አዘዘ (ት. እና ቃ. ፻፲፭፡፣፯–፰)። በአመጽ የተነሳሱ ሰዎች በማሳደዳቸው ምክንያት ይህን ከማድረግ ተወግደው ነበር። በዚያ አመት ጥቅምት ፴፩ (እ.አ.አ.) ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ እና ሌሎች የቤተክርስቲያኗ መሪዎች ታሰሩ፣ እናም በሪችመንድ በፍርድ ቤት ከቀ ረቡ በኋላ በልብርቲ እስር ቤት ውስጥ ታሰሩ። በ፲፰፻፴፰–፲፰፻፴፱ (እ.አ.አ.)፣ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን ከፋር ዌስ ትና ከምዙሪ ሌሎች ቦታዎች ተገደው ወጡ እናም ወደ ኢሊኖይ ሄዱ።

ታላቅ ድርጊቶች፡ የቤተመቅደስ ቦታ ተቀደሰ እናም የማዕዘን ድንጋይ ተነጠፈ። በትምህርት እና ቃል ኪዳ ኖች ውስጥ የታተሙ ሰባት ራዕዮች ተቀበለበት (ክፍሎች ፻፲፫–፻፲፭፣ ፻፲፯–፻፳)። የቤተክርስቲያኗ ስድስተኛ ፕሬ ዘደንት ጆሴፍ ኤፍ ስሚዝ በፋር ዌስት ውስጥ በህዳር ፲፫፣ ፲፰፻፴፰ (እ.አ.አ.) ተወለዱ። ፋር ዌስት በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ ስር እንደ ቤተክርስቲያኗ ጠቅላይ መምሪያ ለአ ጭር ጊዜ አገለገለ።

12. ልብርቲ እስር ቤት

በልብርቲ፣ ምዙሪ ውስጥ የነበረ እስር ቤት፣ በ፲፰፻፳፱ (እ.አ.አ.) አካባቢ። ጆሴፍ ስሚዝ እና ሌሎች አምስት ወንድሞች ፩ ነጥብ ፪ ሜትር ውፍረት ያለው ግድግዳ ዎች ባለው እስር ቤት ውስጥ ከታህሳስ ፩፣ ፲፰፻፴፰ እስከ ሚያዝያ ፮፣ ፲፰፻፴፱ (እ.አ.አ.) ድረስ ታስረው ነበር። (ስድኒ ሪግደን በየካቲት መጨረሻ ላይ ተለቀቀ።) በህ ንጻው በታች ክፍል ወይም ወህኒ ቤት ውስጥ ታስረው እያሉ፣ ብዙ ብርሀን ሳይኖራቸውና ከብርድ መጠበቂ ያም ብዙ ሳይኖራቸው በቀዝቃዛ፣ ሳር በተበተነበት መሬት ላይ ይተኙ ነበር።

ታላቅ ድርጊቶች፣ ነቢዩ ጆሴፍ፣ ከምዙሪ ስለሚሰደ ዱት ብዙ ሺህ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን ሲለምን፣ በደብዳቤ ለቅዱሳን የጻፈውን የጸሎት መልስ ተቀበለ (ት. እና ቃ. ፲፳፩–፲፳፫)።

13. የናቩ አዳራሽ ቤት



ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ እና ቤተሰቡ ወደ አዳራሽ ቤት በነ ሀሴ ፲፰፻፵፫ (እ.አ.አ.) ገቡ። በጓላም በቤቱ በስተምስ ራቅ በኩል ተጨማሪ ክፍሎች ተሰርተው በአጠቃላይ ፳፪ ክፍሎች ነበሩት። ከጥር ፲፰፻፵፬ (እ.አ.አ.) መጀመሪያ ጀምሮ፣ ኤበነዝር ሮቢንሰን ቤቱን እንደ ሆቴል አስተዳደ ረው፣ እናም ነቢዩ ስድስት ክፍሎችን ለቤተሰቡ ጠበቀ። ቤቱ እንደ ናቩ ማህበራዊ ማእከል ያገለግል ነበር። አስ ፈላጊ ታላቅ ሹመቶችን ነቢዩ በእዚህ ይቀበላቸው ነበር።

ታላቅ ድርጊቶች፥ በሰኔ ፳፯፣ ፲፰፻፵፬ (እ.አ.አ.) ነቢዩ ጆሴፍ እና ወንድሙ ሀይረም በካርቴጅ፣ ኢለኖይ በጥይት ተገደሉ፣ እናም ከመቀበራቸው በፊት ሰውነቶቻቸው ወደ እዚህ ቤት ለለቅሶ መጥተው ነበር። ወደ ናቩ ከመም ጣቱ በፊት ጆሴፍ ይኖርበት ከነበረው የፍልጥ እንጨት ቤት በስተምስራቅ በኩል በሚይን ስትሪት ተሻግሮ በሚ ገኘው በቤተሰብ የመቃብር ቦታ ውስጥ ተቀበሩ። ኤማ ስሚዝ በአዳራሽ ቤት ውስጥ እስከ ፲፰፻፫፭ (እ.አ.አ.) ድረስ ኖረች። ከእዚያም ወደ ናቩ ቤት ገባች፣ በእዚያም በ፲፰፻፫፰ (እ.አ.አ.) ሞተች።

14. የነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ የቀይ ሸክላ ሱቅ



በናቩ፣ ኢሊኖይ ውስጥ የሚገኘው እንደገና የተገነባው የጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ የንግድ ቤትና ቢሮ። በናቩ ዘመን ይህ ህንጻ ከሌሎች በሙሉ በላይ አስፈላጊ የሆነ የቤተክርስቲያኗ ህንጻ ነበር። ይህ እንደ አጠቃላይ ሱቅ ያገለግል ብቻ ሳይሆን፣ ይህም የማህብረሰብ፣ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ እና የሀይማኖት ማእከል ነበር። ጆሴፍ ስሚዝ በሁለተኛው ደረጃ ክፍል ውስጥ ቢሮ ነበረው።

ታላቅ ድርጊቶች፥ ቤተመቅደሱ ከመፈጸሙ በፊት፣ የንግድ ቤቱ ታላቅ አዳራሽ የመጀመሪያው ሙሉ የመንፈስ ስጦታዎች እንደተሰጡበት የስነስርዓት ክፍል ይጠቀሙበት ነበር። በመጋቢት ፲፯፣ ፲፰፻፴፪ (እ.አ.አ.)፣ ነቢዩ የቤተክርስቲያኗን ሴቶች እንደ ሴቶች መረዳጃ ማህበር አደራጃቸው።

15. የናቩ ቤተመቅደስ

ቀዳሚው የናቩ ቤተመቅደስ ግራጫ ነጭ በሆነ በእዚያ አካባቢ በሚገኝ ድንጋይ የተሰራ ነበር። ህንጻው ፴፬ ሜትር ረጅም እና ፳፯ ሜትር ስፋት ያለው ነበር። ማማው ከመሬት ፵፰ ሜትር በላይ ነበር። የቤተክርስቲያኗ አባላት ይህን አስደናቂ ቤተመቅደስ ለመገንባት ታላቅ መስዋእት አደረጉ፣ ስራው የተጀመረውም በ፲፰፻፵፭ (እ.አ.አ.) ነበር። አንዳንዶች ለብዙ ወሮች ህንጻውን ለመገንባት ሰሩ፤ ሌሎች ገንዘብን በመስዋዕት ሰጡ። ምንም እንኳን በሙሉ ባይፈጸምም፣ ወደ ምዕራብ ከመሸሻቸው ወሮች በፊት ለስርዓቶች በሚመጡ አባላት እስከሚችለው ድረስ ተሞልቶ ነበር። በእመጽ በተነሳሱ ሰዎች ማስፈራራት ምክንያት ብዙ ቅዱሳን ከናቩ ወጥተው ቢሄዱም፣ ቤተመቅደሱን ለመፈጸም ልዩ ሰራተኞች ወደኋላ ቀር ተው ነበር። በሚያዝያ ፴፣ ፲፰፻፵፮ (እ.አ.አ.)፣ የአስራ ሁለት ሐዋሪያት ቡድን አባላት ሽማግሌዎች ኦርሰን ሀይድ እና ዊልፈርድ ዉድረፍ እና ፳ ሌሎች ይህን የጌታ ቤት ቀደሱ። በመስከረም የቀሩት የቤተክርስቲያኗ አባላት ከናቩ በግድ ሲወጡ ቤተመቅደሱን ትተው ሄዱ፤ ከእዚያም አመጸኛ ሰዎች የተቀደሰ ህንጻውን አረከሱ። ውስጡ የነበረውም በጥቅምት ፲፰፻፵፯ (እ.አ.አ.) በእሳት ተደምስሶ ነበር። እንደገና የተገነባው ቀዳማዊውን የሚመስለው ቤተመቅደስ (በዚህ የሚታየው ፎቶ) ከሰኔ ፳፯–፴፣ ፳፻፪ በፕሬዘደንት ጎርደን ቢ. ሒንክሊ ተቀድሶ ነበር።

ታላቅ ድርጊቶች፣ በጥቅምት ፳፣ ፲፰፻፵፰ (እ.አ.አ.) በመሰብሰቢያው ክፍል አጠቃላይ ጉባኤ ነበር። የመንፈስ ስጦታው በታህሳስ ፲ ቀን ፲፰፻፵፰ ተጀምሮ እስከ የካቲት ፯፣ ፲፰፻፵፱ (እ.አ.አ.) ድረስ ቀጠለ። ከ፲ ሺህ ፲፪ የኋለውኛው ቀን ቅዱሳን የመንፈስ ስጦታቸውን ተቀበሉ፣ እናም ብዙ ለሙታን በወኪል መጠመቅ እና መተሳሰርም ተፈጽሞ ነበር።

16. የካርቴጅ እስር ቤት



በካርቴጅ ከተማ፣ ኢለኖይ ውስጥ የነበረ እስር ቤት።

ታላቅ ድርጊቶች፥ በሰኔ ፳፬፣ ፲፰፻፴፪ (እ.አ.አ.) ጆሴፍ ስሚዝ እና ወንድሙ ሀይረም ስሚዝ ወደ ካርቴጅ በፈረስ ሄዱ። በሰኔ ፳፭ በሀሰት የአገር መክዳት ክስ ወደ እስር ቤት ተጣሉ። በሰኔ ፳፯ ፊታቸውን ጥቁር ቀለም የቀቡ አመጸኛ ሰዎች እስር ቤቱን ሰብረው ገቡ። ጆሴፍ እና ሀይረም በጥይት ተገደሉ፣ እናም ጆን ቴይለርም ቆሰሉ። በሚያስደንቅ ሁኔታም፣ ዊለርድ ሪቻርድ ግን ምንም አል ተጎዱም።

17. ወደ ምዕራብ መሰደድ



ከናቩ፣ ኢለኖይ ለቅቆ መውጣት የሚጀመርበት ጊዜ አላማ የነበረው በመጋቢት እና በሚያዝያ መካከል ነበር፣ ነገር ግን ባመጹት ህዝቡ ፍርሀት ምክንያት ፕሬዘደንት ብሪገም ያንግ ቅዱሳን የምስስጢ ወንዝን በመሻገር ስደ ታቸውን በየካቲት ፩፣ ፲፰፻፴፮ (እ.አ.አ.) እንዲጀምሩ መመሪያ ሰጡ። ፕሬዘደንት ያንግ ለቅዱሳን የሀይማኖት ስጦታዎችን ለማከናወን ወደኋላ ቀሩ እናም እስከ የካቲት መሀከል ድረስ ከናቩ አልወጡም ነበር።

ታላቅ ድርጊቶች፥ ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ ከመሞቱ በፊት እንዲህ ተነበየ፣ “አንዳንዶቻችሁ ከዚህ ሄዳችሁ መኖሪ ያን በመመስረት፣ ከተማዎችን በመገንባት እና ቅዱሳን በሮኪ ተራራዎች መካከል ሀይለኛ ህዝቦች እንዲሆኑ ለማ ድረግ ትረዳላችሁ።” ፲፪ ሺህ የሚሆኑ ቅዱሳን ከየካቲት እስከ መስከረም ፲፰፻፴፯ (እ.አ.አ.) ድረስ ከናቩ ወጡ። ቅዱሳን ከዊንተር ኮርተር ከወጡ በኋላ፣ በአስር፣ ሀምሳ፣ እና መቶ ቡድኖች ተደራጁ፣ እያንዳንዱም በሻምበል ስር ነበሩ (ት. እና ቃ. ፲፭፤ ፲)። በመስከረም ፲፰፻፴፯ (እ.አ.አ.) ስድስት መድፎች የነበሯቸው ፰፻ የሚሆኑ ሰዎች ናቩን ከበቡ። ከብዙ ቀናት ጦርነት በኋላ፣ የቀ ሩት ቅዱሳን ህይወታቸውን ለማዳን እና ወንዙን የመሻ ገር እድል ለማግኘት እራሳቸውን በምርኮነት አሳልፈው ሰጡ። ከአምስት እስከ ስድስት መቶ ወንዶች፣ ሴቶች፣ እና ልጆች ወንዙን ተሻገሩ እናም በወንዙ ዳርም ሰፈሩ። ፕሬዘደንት ብሪገም ያንግ እነዚህን “ደህ ቅዱሳን” ለማ ዳን የሚያድኑ ቡድኖችን ከመደገፊያዎች ጋር ላኩላቸው።

18. የሶልት ሌክ ቤተመቅደስ

የሶልት ሌክ ቤተመቅደስ ከሰሜን ምስራቅ በኩል ሲታይ። የመጀመሪያዎቹ ፈር ቀዳጆ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን ወደ ሶልት ሌክ ሸለቆ ከገቡ በኋላ፣ ፕሬዘደንት ብሪገም ያንግ መሬትን በዱላቸው መትተው እንዲህ አወጁ፣ “በዚህ ቦታ ላይ የእግዚአብሔራችንን ቤተመቅደስ እንገነባ ለን።” ስራውም በየካቲት ፲፭፣ ፲፰፻፶ (እ.አ.አ.) ተጀመረ። በሚያዝያ ፮፣ ፲፰፻፶ (እ.አ.አ.) የማዕዘን ድንጋዩ ተነጠፈ። ቤተመቅደሱም ከአርባ አመት በኋላ በሚያዝያ ፮፣ ፲፰፻፷፯ (እ.አ.አ.) ተፈጸመ እናም ተቀደሰ። ቀዳሚ አመራር እና አስራ ሁለቱ ሐዋሪያት ለመወያየት እና የእ ግዚአብሔርን መንግስት ለመገንባት እና ለማስተዳደር ከጌታ መመሪያን ለማግኘት በየሳምንቱ በእዚህ ይገናኛሉ።

ታላቅ ድርጊቶች፥ ከአስተዳደሪያዊ አዋጅ ፪ በተጨማሪ፣ ጌታ የቤተክርስቲያኗን ፕሬዘደንቶች እና አጠቃላይ ባለ ስልጣኖችን በዚህ ቦታ ላይ የራዕይ መንፈስን አፍስሶላ ቸዋል። በቅርብም፣ ቀዳሚ አመራር እና የአስራ ሁለቱ ሐዋሪያት ሸንጎ በአንድ ድምፅ “ቤተሰብ፣ ለአለም የተ ላለፈ አዋጅ” ተቀብለው አሳትመዋል። ለህያዋን ይሁን ለሙታን የሚከናወነው የቤተመቅደስ ስነስርዓቶች የሚ ልዮኖችን ህይወቶች ባርከዋል።

AMHARIC